إِنَّا نَحْنُ نَزَّلْنَا الذِّكْرَ وَإِنَّا لَهُ لَحَافِظُونَ

إِنَّهُ لَقُرْآنٌ كَرِيمٌ فِي كِتَابٍ مَكْنُونٍ لَا يَمَسُّهُ إِلَّا الْمُطَهَّرُونَ تَنْزِيلٌ مِنْ رَبِّ الْعَالَمِينَ

ይህንን የተከበረ የቁርኣን ትርጉም እንዲታተም የፈቀዱት የሁለቱ የተከበሩ መስጊዶች አስተዳዳሪ
ንጉስ ሳልማን ቢን አብዱልዐዚዝ ኣል ሳዑድ የሳዑዲ ዓረቢያ ንጉስ ናቸው።

تشرّف بالأمر بطباعة هذه الترجمة لمعاني القرآن الكريم
خادم الحرمين الشريفين الملك سلمان بن عبدالعزيز آل سعود
ملك المملكة العربية السعودية

وَقفٌ لِلهِ تعالى من خادم الحرمين الشّريفَين
الملك سَلمان بن عَبد العَزيز آل سُعُود
ولا يجُوز بيعُه
يُـوزّع مَجّانًا

# ترجمة معاني القرآن الكريم

## إلى اللُّغةِ الأَمهَرية

إعداد

الشَّيخ : مُحمَّد زَيـن زَهر الدّين خَليل

مُجمّع الملك فهد لطباعة المصحف الشّريف
بالمدينة المنوّرة

የሁለቱ የተከበሩ መስጊዶች አስተዳዳሪ ከንጉስ
ሳልማን ቢን አብዱላዚዝ አል ሳዑድ ለአላህ ወቅፍ የተደረገ ነው።
መሸጥ የተከለከለ ነው
በነጻ የሚከፋፈል

# የታላቁ ቁርኣን መልዕክቶች
# የአማርኛ ትርጉም

አዘጋጅ፡
ሸይኽ ሙሐመድዘይን ዘህረዲን ኸሊል

በመዲና አል ሙነወራህ በሚገኘው የንጉስ
ፈህድ የተከበረ ቁርኣን ማተሚያ ማዕከል

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

# مقدمة

بقلم معالي الشيخ الدكتور

**عبد اللطيف بن عبد العزيز بن عبد الرحمن آل الشيخ**

وزير الشؤون الإسلامية والدعوة والإرشاد

المشرف العام على المجمع

الحمد لله رب العالمين، القائل في كتابه الكريم:

﴿... **قَدۡ جَآءَكُم مِّنَ ٱللَّهِ نُورٞ وَكِتَٰبٞ مُّبِينٞ**﴾.

والصلاة والسلام على أشرف الأنبياء والمرسلين، نبينا **محمد** صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيۡهِ وَسَلَّمَ القائل: «**خيركُم مَن تعلَّم القرآن وعلَّمه**».

أما بعد:

فإنفاذاً لتوجيهات خادم الحرمين الشريفين الملك سلمان بن عبدالعزيز آل سعود -حفظه الله- بالعناية بكتاب الله، والعمل على تيسير نشره، وتوزيعه بين المسلمين في مشارق الأرض ومغاربها، وتفسيره وترجمة معانيه إلى مختلف لغات العالم.

وإيماناً من وزارة الشؤون الإسلامية والدعوة والإرشاد بالمملكة العربية السعودية، بأهمية ترجمة معاني القرآن الكريم إلى جميع لغات العالم المهمة؛ تسهيلاً لفهمه على المسلمين الناطقين بغير العربية، وتحقيقاً للبلاغ المأمور به في قوله صَلَّى ٱللَّهُ عَلَيۡهِ وَسَلَّمَ: «**بلِّغوا عنِّي ولو آية**».

وخدمةً لإخواننا الناطقين باللغة الأمهرية، يطيب لمجمع الملك فهد لطباعة المصحف الشريف بالمدينة المنورة، أن يقدم للقارئ الكريم هذه الترجمة إلى اللغة الأمهرية، التي قام بها فضيلة الشيخ: **محمد** زين زهر الدين خليل، وراجعها من قبل المجمع: سعيد أيوب **محمد**.

ونحمد الله سُبۡحَانَهُۥوَتَعَالَىٰ أن وفق لإنجاز هذا العمل العظيم، الذي نرجو أن يكون خالصاً لوجهه الكريم، وأن ينفع به الناس.

إننا لندرك أن ترجمة معاني القرآن الكريم -مهما بلغت دقتها- ستكون قاصرة عن أداء المعاني العظيمة التي يدل عليها النص القرآني المعجز، وأن المعاني التي تؤديها الترجمة إنما هي حصيلة ما بلغه علم المترجم في فهم كتاب الله الكريم، وأنه يعتريها ما يعتري عمل البشر كلّه من خطإ ونقص.

ومن ثم نرجو من كل قارئ لهذه الترجمة أن يوافي **مجمع** الملك فهد لطباعة المصحف الشريف بالمدينة النبوية، بما قد يجده فيها من خطإ أو نقص أو زيادة؛ للإفادة من الاستدراكات في الطبعات القادمة إن شاء الله.

والله الموفق، وهو الهادي إلى سواء السبيل، اللَّهُمَّ تقبل منا إنك أنت السميع العليم.

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**መቅድም «ሀ»**

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህበጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።**

ምስጋና ሁሉ ለዐለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይሁን። ለዚያም በተከበረው ቁርአኑ ዉስጥ «ከአላህ ብርሃንና ግልፅ የሆነው መፅሐፍ መጣላችሁ» ላለው ጌታ (ምስጋና ይገባው)።

ሶላትና ሰላምታ ከመልዕክተኞች ሁሉ ምርጥ ለሆኑትና «ከናንተ መካከል ምርጥ ማለት ቁርኣንን ተምሮ ያስተማረ ነው» ላሉት ለታላቁ ነቢያችን ሙሐመድ ይሁኑ።

በመቀጠል፡- ከሁለቱ ቅዱስ መስጊዶች አስተዳደር ከንጉስ ሰልማን ብን ዐብዱል ዐዚዝ ኣል ሱዑድ አላህ ይጠብቃቸዉና የአላህን ቁርኣን በመንከባከብ፤ በማስፋፋት ከምስራቅ እስከ ምዕራብ በሚገኙ ሙስሊሞች መካከል በማሰራጨት፤ ትርጉሙን በማብራራት ወደ ዐለም ቋንቋዎች በመተርጎም ላይ ትኩረት እንድናደርግ የተሰጠውን መመሪያ ለመ ተግበር፤

በሳዑዲ ዐረቢያ የሃይማኖት ጉዳዮች፤ የጥሪና የመምሪያ ጉዳዮች ሚኒስቴርም ቁርኣ ንን ዐረበኛ ለማያውቁ ሙስሊሞች በቀላል እንዲረዱ ባለው ጠንካራ እምነት፤ ነቢዩ ሙሐመድ «አንድን አንቀፅ እንኳን ቢሆን ከኔ የሰማችሁትን አድርሱ» በማለት ያዘዙትን ነብያዊ ትእዛዝ ለመተግበር፤

የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪ ወንድሞቻችንን ለመርዳት በማሰብ፤ በብርሃኗ ኢስላማዊ የመዲና ከተማ የሚገኘው የተከበረው የታላቁ ቁርኣን ማተሚያ ማዕከል ይህን በሸይኽ ሙሐመድዘይን ዘህረዲን ኸሊል ተተርጉሞ ከማዕከሉ በኩል በሸይኽ ሰዒድ አዩብ ሙሐመድ የታረመዉን የአማርኛ የቁርኣን ትርጉም ሲያቀርብ በሙሉ ደስታ ነው።

በፍፁምነት የተሰራ እንዲሆንልን እና ለሰዎችም ጠቃሚ እንዲሆን የምንመኘዉን ይህን ታላቅ ተግባር ለማበርከት ያስቻለንን አላህን እናመሰግነዋለን።

በእርግጥም ቁርኣንን መተርጎም የቱንም ያህል ጥንቃቄ ቢደረግም ያ የተከበረውን ከአላህ የወረደዉን የዐረበኛውን ቁርኣን መልዕክት ሙሉ በሙሉ ማስተላለፍ እንደማ ይቻል ጠንቅቀን እናውቃለን። ትርጉም ማለት ተርጓሚው ከቁርኣን የተረዳው ማለት ነዉና።

ስለዚህ ስራችን የሰዎች ስራን ሁሉ የሚያጋጥሙ ነገሮች ሁሉ ሊገጥመው ይችላልና ይህን ትርጉም ለሚያነቡ ሁሉ ለሚያገኙት ስህተት፤ ጭማሬ፤ ጉድለት፤ ለመዐከሉ እን ዲልኩልን ተስፋችን ፅኑ ነው።

ምክኒያቱም ለወደፊት በሚደረጉ ህትመቶች ላይ ለማረም ያስችለን ዘንድ ነው።ወደ ቀናዉ መንገድ የሚመራዉና በትክክለኛው መስመር የሚያስከደውም አላህ ብቻ ነው። አላህ አንተ ሁሉን ሰሚና ሁሉን አዋቂ ነህና ስራችንን ተቀበለን።

**ክቡር ዶ/ሸይኽ ዐብዱለጢፍ ብን ዐብዱል ዐዚዝ ብን ዐብዱ ረህማን ኣሊ-ሸይኽ.**
**የሃይማኖት ጉዳዩች፤የጥሪና የመምሪያ ጉዳዮች ሚኒስቴር ሚኒስቲር እና የመዐከሉ**
**የበላይ ጠባቂ**

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

## መቅድም «ለ»

### በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህና አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።

የተርጓሚው መግቢያ:-

ቁርኣን የአላህ ቃል ነው። ቁጥር ስፍር የሌለው ምስጋና ለዐለማቱ ጌታ ለአላህ ይሁን። ሶላትና ሰላም በነቢዩ ሙሐመድ፤ በንፁሃን ዘመዶቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን። እነሱን በመከተል ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ሁል ጊዜም ይህን ቁርኣን በመማርና በመተግበር፤ በትክክል ለህዝቡ በማድረስ ላይ ደፋ ቀና ለሚሉ ሁሉ ተመሳሳዩ እድል ይሁንላቸው። በመቀጠል:-

ሰዎች ዉድ ጊዜያቸዉን የሚያሳልፉበት፤ ወርቃቸዉንና ብራቸዉን ምስዋእት ሊከፍ ሉለት የሚገባው ነገር ቢኖር ቁርኣን ነው። በመሆኑም እኔም አቅሜ ባይሆንም ለሀገሬ ህዝብ በተለይም የአማርኛን ቋንቋ አንብቦ ለመረዳት አቅም ላለላቸው እና በአንፃሩም የዐረበኛን ቋንቋ እንደልብ አንብበው መረዳት ለማይችሉ -ዐረበኛን እንዲያውቁ አደራ እያልኩ- የቁርኣንን መልዕት በትንሹም ቢሆን ለመረዳት ጥቂትም ቢሆን በር ያሳያል ያልኩትን ሁሉ በዚህ መፅሐፍ ዉስጥ ሞክሪያለሁ። እናም ይህ ቀለልና አጠር ያለ የቁር ኣንን የአማርኛ ትርጉሙን፤ አንዳንድ አናቅፅ የወረዱበትን ምክኒያት፤ የተሻሩ አናቅፅን፤ የአናቅፅን ጉልህ አስተምህሮት የዳሰሰ በይበልጥ እምነት ነክ ነገሮች ላይ ትኩረት ያደረ ኩበትን (የአረህማን ችሮት የቁርኣን አጭር ትርጉምና አስተምህሮት) በማለት የሰየም ኩትን መፅሐፌን አቅርቢያለሁ።

ማስረጃ የሌላቸው ማብራሬያዎችና ዘገባዎች እንደዚሁም ሳላስተዉለው ያመለጠኝ የቃል የፊደል የአገላለጽ ስህተት ካለ አስትያየታችሁን በድርጂቱ አማካኝነት ብትልኩ ልኝ ምስጋናየ የላቀ ነው። አላህ ከፈቀደ በሁለተኛው እትም ላይም ለምናደርገው የማ ሻሻያ ጥረት ይረዳናል።

ስለሆነም ከላይ የተጠቀሱትን ጭማሬዎች በቡኒ ቀለም ተለይተው መቅረባቸዉን እያ ሳሰብኩ ያን (ፈትሁ አር-ረሕማኒ አር-ረሒም ፊመዓኒ ወዱሩሲል ቁርኣኒል ከሪም) የተ ባለዉን ትልቁንም በሰላም አስጨርሶኝ ለማሳተም እንዲያበቃኝ አላህን እማፀነዋለሁ።

**መልካም ንባብ ይሁንላችሁ።**
**ሙሐመድዘይን ዘህረዲን ኸሊል**

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ርኅሩኅ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

## የተከበረው ቁርኣን መልእክት ትርጉሞች መቅድም፡-

### መንደርደሪያ፡-

የተከበረው ቁርኣን ለዓለማት እዝነት ይሆን ዘንድ በመልክተኛው ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ ኃያሉ አላህ ከእነ ፊደሎቹና መልእክቶቹ ያወረደው የአላህ የራሱ ቃል ነው።

ቁርኣን የአላህን ምንዳ አብሳሪ፣ ከቅጣቱ አስጠንቃቂ፣ በአላህ ፍቃድም አብሪ ወደ ሆነው ቀጥተኛ መንገድ ተጣሪ የሆነ የአላህ ቃል ነው።

ከዚህ በመቀጠል ስለ ተከበረው ቁርኣን እና በውስጡ ያካተታቸውን ተልእኮዎች አስመል ክቶ አጠር ያለ ማስተዋወቂያ ይቀርባል።

## በጥቅሉ የተከበረው ቁርኣን ምንድነው?

### አንደኛ፡- የተከበረው ቁርኣን ምንነት፣ የስሞቹ እና የባሕርያቱ መግለጫ፡-

የተከበረው ቁርኣን የአላህ መልክተኛ በሆኑት በመሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የወረደ፣ ቃላቱም ሆነ መልእክቶቹ በወሕይ የተገለጸ የኃያሉ አላህ ንግግር ሲሆን፣ በመጽሐፍ ላይ ተጽፎ የሰፈረ፣ ከትውልድ ወደ ትውልድ የተላለፈ፣ በንባቡ አማካኝነት አላህን የምንግገዛበት የአላህ ቃል ነው።

በወሕይ ተገልጾ በመልክተኛው ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የወረደውን ቁርኣን "ቁርኣን" በሚል ስያሜ የሰየመው ኀያሉ አላህ እራሱ ነው። አላህ እንደዚህ ይላል:-

"እኛ ቁርኣንን ባንተ ላይ ማውረድን እኛው አወረድነው።" አል-ኢንሳን፥ 23

የቁርኣን መሠረታዊው ቁም ነገር መነበቡ እና ችላ አለመባሉ ነው።

ልክ እንደዚሁ አላህ (ሱ . ወ) ቁርኣንን "መጽሐፍ" (አል-ኪታብ) በሚል ሰይሞታል።አላህ እንደዚህ ይላል፡- "እኛ በሰዎች መካከል አላህ ባሳወቀህ ልትፈርድ ወደአንተ መጽሐፍን በውነት አወረድን፤ ለከዳተኞችም ተከራካሪ አትሁን።" አል-ኒሳእ፥ 105

ቁርኣን በባሕሪዩ በጽሑፍ የሚሰፍርና ቸል የማይባል ነው።

ኀያሉ አላህ ተከበረው ቁርኣንን እውነትና ሐሰትን ገላጭ (ፉርቃን)፣ ተግሳጽ (ዚክር)፣ መመሪያ (ሁዳ)፣ ብርሃን (ኑር)፣ ፈውስ (ሺፋእ)፣ ጥበበኛ (ሐኪም) መግገሰጫ (መውዒዛ) በሚሉና የቁርኣንን ኀያልነትና ምሉዕ የሆነ ተልዕኮውን በሚገልጹ በሌሎችም የባሕርይ ስሞቹ ገልጾታል።

ሌላው የቁርኣን ስም የሆነው "አል-ሙስሐፍ" የሚለው ቃል የተወሰደው፣ የተከበረው ቁርኣን በላዩ ላይ ተጽፎ የሰፈረበት "ሱሑፍ" ከሚለው ቃል ነው። ለተከበረው ቁርኣን ይህንን ስያሜ የሰጡት የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሶሓባዎች ሲሆኑ፣ በገጾቹ የተከበረው ቁርኣን ተጽፎ የሰፈረበትን መጽሐፍ ለማመልከት የተጠቀሙት ቃል ነው።

የተከበረው ቁርኣን በመልአኩ ጂብሪል አማካኝነት ከኀያሉ አላህ በራዕይ ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) የተወረደ የአላህ ንግግር ነው። አላህ እንደዚህ ይላል:-

"እርሱም (ቁርኣን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው። እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጂብሪል) አወረደው። ከአስፈራሪዎቹ (ነቢያት) ትሆን ዘንድ በልብህ ላይ (አወረደው)። ግልጽ በሆነ ዐረብኛ ቋንቋ።" አል-ሹዐራእ፥ 192-195

የኀያሉ አላህን ቃል ከመልአኩ ጂብሪል በመቀበሉ ረገድ ነቢዩ መሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ከነቢያት መልክተኞች የመጀመሪያው ሰው አይደሉም። ከእርሳቸው በፊት የነበሩት ነቢያት መልክተ ኞች ሁሉ የአላህን ቃል በራዕይ የሚቀበሉት በመልአኩ ጂብሪል አማካኝነት ነበር።

ኀያሉ አላህ የእርሱን ቃል ለመቀበል ታላቅ ዓላማ የፈለገውን ሰው ይመርጥና ያጭ ነበር። አላህ እንደዚህ አለ፡-

**“አላህ ከመላእክት ውስጥ መልክተኞችን ይመርጣል፤ ከሰዎችም (እንደዚሁ)፤ አላህ ሰሚ ተመልካች ነው።” አል-ሐጅ፡ 75**

ፍጥረታት በሙሉ የርሱ እንደመሆናቸው መጠን፣ ለዚህ ታላቅ ዓላማ ማን እንደሚመጥንና እንደማይመጥን ኀያሉ አላህ በሚገብባ ያውቃል። አላህ እንደዚህ አለ፡-

**“ጌታህም የሚሻውን ይፈጥራል፤ ይመርጣልም፤ ለነሱ (ለሰዎቹ) ምርጫ የላቸውም፤ አላህ ከማይግገባው ሁሉ ጠራ። ከሚያጋሯቸውም ላቀ።” አል-ቀሰስ፥ 68**

### ሁለተኛ፡- የተከበረው ቁርኣን መውረድ

የቁርኣን ራዕይ በአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ መውረድ የጀመረው ዕለተ-ሰኞ፣ በወርሃ ረመዷን፣ በአሥራ ሰባተኛው ቀን፣ በመካ ከተማ አቅራቢያ በሚገኝ ተራራ ውስጥ ባለ “ሒራእ” በተባለ ዋሻ ውስጥ በ610 እ.ኤ.አ መልአኩ ጂብሪል የሚከተለውን የቁርኣን አናቅጽ ይዞ መምጣት የጀመረ ጊዜ ነው፡-

**“አንብብ በዚያ (ሁሉን) በፈጠረው ጌታህ ስም። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም) አንብብ፤ ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን። ያ በብዕር ያስተማረ ሰውን ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ሲሆን።” አል-ዐለቅ ፥1-5**

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የቁርኣን አናቅጽ በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ የወረዱ የመጀመ ሪያዎቹ የተከበረው ቁርኣን ቃል ናቸው።

ከዚህ በኋላ በሆነው ሁኔታ በመደናገጥና ለነፍሳቸውም በመፍራት የአላህ መልክተኛ (ሰ. ዐ.ወ) ወደ ቤታቸው ተመለሱ። ያጋጠማቸውን ክስተት የምእመናን እናት ለሆኑት ለባለቤ ታቸው ለኸዲጃ ቢንት ኹወይሊድ ይነግሯቸዋል። “እኔ ለነፍሴ ፈርቻለሁ።” ይላሉ ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ)። ኸዲጃም መልሰው “በፍጹም አይፍሩ! አብሽሩ። በአላህ እምላለሁ! አላህ እርሶን ፈጽሞ አያሳፍርዎትም። እርሶ የዝምድና ትስስር ገመዶችን ያጠብቃሉ። ንግግሮ እውነተኛ ነው። እንግዳዎን ያከብራሉ። አቅመ ደካማዎችን ይረዳሉ። የተቸገሩ ሰዎችን ችግር አዳም ጠው ይፈታሉ።” አሏቸው።

እመቤት ኸዲጃ ጥበብና በሳል ምክረ ሐሳብ ወደታደለው ወረቃ ቢን ነውፈል ወደተባለው አዛውንት የአላህ መልክተኛን (ሰ.ዐ.ወ) ይዘዋቸው ሄዱ። እንደደረሱም ኸዲጃ ለወረቃ እንደ ዚህ አሉት “አጎቴ ሆይ! እስኪ ይህ የወንድምህ ልጅ የሚልህን ስማ!”

ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) የተመለከቱትንና ያጋጠማቸውን ነገር ሲነግሩት ወረቃ ቢን ነውፈል እንደዚህ አለ “ይህ ወደ ነቢያት የአላህን ቃል ይዞ የሚመጣው መልአኩ ጂብሪል ነው።

በሙሳ ላይ ያወረደውም እርሱ ነው። ምነው ወጣት በሆንኩ ኖሮ! ሕዝቦችህ ከሐገር (ከመካ) ሲያስወጡህ በሕይወት በቆየሁና አብሬህ በኖርኩ ኖሮ!”

የአላህ መለእክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ይሄንን ሲሰሙ “እነርሱ ያሳድዱኛልን?” በማለት ጠየቁ። ወረቃም “አዎን! አንተ ይዘህ የተነሳኸውን ዓይነት ተልእኮ ይዞ የተነሳ ነቢይ ሁሉ ጠላት ያልተነሳበት የለም። ነቢይ ሆነህ በተነሳህ ጊዜ በሕይወት ካለሁ ከጎንህ ቆሜ እሰለፋለሁ።”

አለ። ነገር ግን ወረቃ በዚህ መልኩ ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ጋር በተገናኘ በአጭር ጊዜ ውስጥ ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ።

ቀደም ሲል በነበሩት ነቢያት (ዐ.ሰ) ላይ እንደወረደው ሁሉ ተከበረው ቁርኣን በአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ በአንዴ ሙሉ ለሙሉ አልወረደም። ይልቁንም በእርሳቸው ላይ ቁርኣኑ የወረደው በሃያ ሦስት ዓመታት ውስጥ በተለያዩ ጊዜያት ነበር። አንዳንዴ አንድ ሙሉ ሱራ አንዳንዴ ደግሞ ከአንድ ሱራ ውስጥ የተወሰኑ አናቅጽ እየተከፋፈሉ ይወርዱ ነበር።

ተከበረው ቁርኣን በዚህ መልኩ በተለያዩ ጊዜያት እየተከፋፈለ ሊወርድ የቻለበት መሠረታዊ ጥበብና ምክንያት፤ የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ቀልብ ጽኑ ዕና የጠነከረ እንዲሆን ለማድረግ እንዲሁም መላኩ ጂብሪል በተለያየ ጊዜ ወሕይ ይዞ እየወረደ በአዲስ መልኩ የኀይል እገዛ ለማድረግ በሚል ነበር።

በመጀመሪያዎቹ የተልእኮ ዓመታት ከጣዖታውያኑ ዘንድ የሚደርስባቸውን መከራ ለመቋቋም የኀይል እገዛ ያስፈልጋቸውና ማጽናኛ ያሻቸው ስለነበር ይህ እንዲሆን ተደረገ። ኀያሉ አላህ ይህንን ጉዳይ በማስመልከት እንደዚህ ይናገራል፡-

**“እነዚያ የካዱትም፡- ቁርኣን በርሱ ላይ ለምን በጠቅላላ አንድ ጊዜ አልተወረደም አሉ፤ እንደዚሁ በርሱ ልብህን ልናረጋ (ከፋፍለን አወረድነው) ቀስ በቀስ መለያየትንም ለየነው።”**
**አል-ፉርቃን፥ 32**

ተከበረው ቁርኣን በዚህ መልኩ በተለያዩ ጊዜያት ተከፋፍሎ እንዲወርድ መደረጉ ሌላም ከፍ ያለና ከልምምድ እንዲሁም ከስልጠና ጋር የተያያዘ ጥበብም ነበረው። ይኸውም ሙእሚኖች ቀስ በቀስ ቅደም ተከተሉን በጠበቀ ሁኔታ ዕውቀት እንዲገበዩና ሕግጋቱን እንዲተገብሩት በሚል ዓላማ ነው።

በቀላሉ የቁርኣንን ዕውቀት እንዲገበዩና ግንዛቤን እንዲጨብጡ፣ ሰምጠው ከነበሩበት የመሐይምነት፣ የክህደት፣ የሺርክ ጨለማዎች ወጥተው ወደ ኢማን፣ ተውሒድና ዕውቀት ብርሃን እንዲሸጋገሩ ቁርኣኑ ቀስ በቀስ እንዲወርድ ተደረገ።

### ሦስተኛ፡- ተከበረው ቁርኣን በጽሑፍ መልክ መመዝገቡ፡-

ቁርኣን ባለበት ተጠብቆ እንዲኖር ከማድረጊያ ዘዴዎች ውስጥ አንዱ በጽሑፍ ሰፍሮ እንዲቀመጥ የማድረጉ ጉዳይ ነው። በጽሑፍ ሰፍሮ ያልተቀመጠ ንግግር ሊረስሳ የሚችልበት ዕድሉ ሰፊ ነው።

ተከበረው ቁርኣን እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ ለዓለማት መመሪያ ይሆን ዘንድ የወረደ እንደመሆኑ መጠን በጽሑፍ ሰፍሮ የመቀመጡን ጉዳይ የግድ ያደርገዋል።

ተከበረው ቁርኣን በነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ዕይታና ቁጥጥር ስር ሆኖ በጽሑፍ ሰፍሮ የመቀመጥ ዕድል አግኝቷል። አንዳንድ የመጻፍ ችሎታ ያላቸው ሶሓባዎችን የወሕይ ጸሓፊያን እንዲሆኑ በማድረግ የተከበረው ቁርኣን ቃሎችን በጽሑፍ እንዲያሰፍሩ አዝዘዋቸዋል። ከእነዚህ የወሕይ ጸሓፊያን ውስጥ አንሷሪ የሆነው ዘይድ ቢን ሳቢት ዋንኛ ተጠቃሽ ነው።

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ምን ጊዜም ራዕይ በወረደላቸው ቁጥር እራሳቸው በቀልባቸው ጠብቀው ካኖሩት በኋላ አንዱ ጸሓፊያቸውን በመጥራት የወረደላቸውን ነግረውት እንዲጽፈው ያደርጋሉ፡ “እነዚህን አናቅጽ እንደዚህ እንደዚያ የሚለው ጉዳይ በተወሳበት ምዕራፍ ውስጥ አስፍሩት።” ይሏቸዋል። ለምዕራፉም የስም ስያሜ ይሰጡታል።

ስያሜ በሰጡት ምዕራፍ ውስጥ አናቅጽ እንዲጽፉ ያዝዟቸዋል። ከዚያም የወረደውን የተከበረው ቁርኣን ቃል ሶሓባዎቹ በቃላቸውና በቀልባቸው ጠብቀው እንዲያኖሩትና እንዲማሩት ያዝዟቸዋል። የተከበረው ቁርኣን ሙሉው ክፍል ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በሕይወት እያሉ በዘመኑ በነበረው የጽሕፈት መሳሪያ በጽሑፍ ሰፍሮ ተቀምጧል።

መልአኩ ጂብሪል በዓመት ለአንድ ጊዜ ያክል ሙሉውን የተከበረው ቁርኣን ክፍል ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ያስጠናቸው ነበር። የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ኅልፈተ-ሕይወት በተፈጸመበት ዓመት ደግሞ መላእኩ ጂብሪል ሙሉውን የተከበረው ቁርኣን ክፍል ለሁለት ጊዜያት ለነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) አስጠንቷቸዋል።

ጂብሪል ለሁለት ጊዜያት ያክል ሲያስጠናቸው የተከበረው ቁርኣን ምዕራፎችና አናቅጽ ቅደም ተከተላቸው በአሁኑ ሰዐት በሙስሊሞች እጅ ባለው መልኩ መሆኑ የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ይህንኑ በማስመልከት ኀያሉ አላህ እንደዚህ ተናግሯል፡-

“በርሱ (በቁርኣን ንባብ) ልትቸኩል ምላስህን በርሱ አታላውስ። (በልብህ ውስጥ) መሰብሰቡና ማንበቡ በኛ ላይ ነውና። ባነበብነውም ጊዜ (ካለቀ በኋላ) ንባቡን ተከተል። ከዚያም ማብራራቱ በኛ ላይ ነው።” አል-ቂያማህ፡ 17-18

“(ቁርኣንን) በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም።” አል-አዕላ፥ 6

### አራተኛ፡- ተከበረው ቁርኣን ተሰብስቦ በአንድ መጽሐፍ መስፈሩ፡-

የነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) ኅልፈተ-ሕይወት ከተፈጸመ በኋላ፣ ቁርኣንን በቃላቸው የሚያውቁ ሰዎች በሞት ሲለዩ ወይም ቁርኣን የተጻፈባቸው የተለያዩ ነገሮች በመጥፋት ምክንያት ከቁርኣኑ ክፍሎች የተወሰኑቱ እንዳይሰወሩ በመስጋት ታላቁ ኸሊፋ አቡበከር አል-ሲዲቅ በተደራጀ መልኩ ቁርኣን በመጽሐፍ መልክ ተጽፎ እንዲቀመጥ ኸሊፋዊ ትእዛዛቸውን ደነገጉ። ኸሊፋው ለዚህ ታላቅ ሓላፊነት የወሕይ ጸሓፊ የሆነው ዘይድ ቢን ሳቢትን ሾሙት።

ዘይድ ሓላፊነቱን ከፈጸመ በኋላ ሥራው በደንብ ተገምግሞ፣ በወቅቱ በነበሩት የጽሕፈት መሣሪያዎች ላይ ከተጻፉትና ቁርኣንን በቃላቸው ይዘው ከነበሩ ሶሓባዎች ጋር ካለው የቁርኣን ይዘት ጋር በሚገባ ተመሳክሮ፣ ትክክለኛነቱ ከተረጋገጠ በኋላ በመጽሐፍ መልክ ተጽፎ የተደራጀው ጥራዝ እንዲጸድቅ ተደርጎ፣ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ በአቡበክር አል-ሲዲቅ ቤት እንዲቀመጥ ተደረገ።

ከአቡበክር ኅልፈት በኋላ ሁለተኛው ኸሊፋ ዑመር ቢን አል-ኸጣብ ዘንድ ተቀመጠ። ከእርሳቸው ኅልፈት በኋላ ደግሞ የዑመር ሴት ልጅ የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባለቤት የሆነችው የምእመናን እናት ሐፍሷ ቤት እንዲቀመጥ ተደረገ።

ኢስላም ወደ ተለያዩ አገራት በስፋት በመሰራጨቱ ምክንያት፣ ሙስሊሞች ሊያነብቡት የሚገባባ በቂ የሆኑ ቅጂዎች አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣ የተወሰኑ ሶሓባዎች ሙስሊሞች አንድ ወጥ የሆነና ዋነኛ ማጣቀሻ ሊሆናቸው የሚችል የተለያዩ ቅጂዎች መዘጋጀት እንደሚኖርባቸው ለኸሊፋው ዑስማን ማሳሰቢያ ይሰጣሉ።

ኸሊፋው ዑስማንም በማሳሰቢያው በመስማማት፣ በአቡበክር አል-ሲዲቅ ዘመን የተዘጋጀውና በመጽሐፍ መልክ ተጽፎ የተደራጀውን ጥራዝ መሠረት አድርገው የተለያዩ የቁርኣን ቅጂዎችን እንዲያዘጋጁ፣ ቁርኣንን በቃላቸው የሚያውቁና የጽሑፍ ችሎታ ያላቸው የሶሓባ ስብስቦችን ከእነዚህ ውስጥ ዋናው ደግሞ ዘይድ ቢን ሳቢትን ያደራጁና ይህኑን ሓላፊነት እንዲወጡ ትእዛዝ ይሰጣሉ።

በዚህ መልኩ የተደራጁት ሶሓባዎች በአቡበክር ዘመን ከተዘጋጀው መጽሐፍ በመቅዳት ብዛት ያላቸው ቅጂዎችን አዘጋጁ። ከዚያም እነዚሁ ብዛት ያላቸው ቅጂዎች ወደተለያዩ ታላላቅ የኢስላም ጠቅላይ ግዛቶች እንዲላኩ ተደርጎ፣ ሙስሊሞች እነዚህኑ መሠረት አድር ገው ቅጂዎች እንዲያዘጋጁ ትእዛዝ ተሰጠ።

በአሁኑ ሰዐት በዓለም ላይ የሚገኘኘው የቁርኣን ቅጂ፣ በእጅ የሚከተበውም ሆነ በኅትመት ማሽን የሚታተመው ሁሉ፣ ዋና መሠረቱን አድርጎ የተቀዳው ቀደም ሲል በተጠቀሰው መልኩ ወደተለያዩ የኢስላም ጠቅላይ ግዛቶች ከተላኩት ቅጂዎች ላይ ነው። ይዘቱም ሆነ ቅደም ተከተሉ ከእነዚህ የመጀመሪያ ቅጂዎች ጋር ልዩነት የለውም።

እስካለንበት ዘመን ድረስ ሙስሊሞች የተለያዩ ዘመኑ ያፈራቸው የኅትመት ዘዴዎችን በመ ጠቀምና በመተግበር “ረስም አል-ዑስማኒ” በሚል የሚታወቀውንና በኸሊፋው ዑስማን ዘመን በጽሑፍ የሰፈረውን ተከበረው ቁርኣን እንዳለ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ ለማተምና ለማ ሰራጨት ከፍተኛ ትኩረትና ጥረት ያደርጋሉ።

በመዲነቱል ሙነወራ ከተማ የሚገገኘውና “መሊክ ፈህድ” የተሰኘው የኅትመት ድርጅት፣ ከላይ በተጠቀሰው መልኩ ተከበረው ቁርኣንን አሳምሮ በማተሙ ረገድ ከፍተኛ ትኩረትና ጥረት ከሚያደርጉት ታዋቂና ዝነኛ የኅትመት ድርጅቶች ውስጥ አንዱ እንጂ ሌላ አይደ ለም።

የንጉሣዊት ሱዑድ ዓረቢያ ባለ ሥልጣናት በዚህ ረገድ ያላቸው ትኩረትና ጥረትም ሙስ ሊሞች ዘመናዊ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ የኅትመትና የጥራዝ ጥራቱን በከፍተኛ ሁኔታ የጠበቀ የተከበረው ቁርኣን ቅጂ በቀላሉ እንዲያገኙ ማገልገል እና ማስቻል ነው።

### አምስተኛ፡- በቅደም ተከተልና በየክፍሎቹ (ጁዝእ) ማስቀመጥ፡-

የተከበረው ቁርኣን የሚጀምረው በአል-ፋቲሐ ምዕራፍ ሲሆን የሚጠናቀቀው ደግሞ በአል-ናስ ምዕራፍ ነው። በጥቅሉ አንድ መቶ ዐሥራ አራት (114) ምዕራፎች አሉት። ይህንን ሁኔታ ማንም ሊለውጠውና ሊቀይረው የማይቻለው ወይም “ተውቂፊይ” ነው።

ይህም ማለት ቅደም ተከተሉ በዚህ መልኩ የተዋቀረው ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) በደነገጉት መልኩ በመሆኑ ማንም ሊለወጠውና ሊቀይረው አይችልም ማለት ነው። ቅደም ተከተሉ የተዋቀ ረው ቁርኣኑ በወረደበት አግባብ አይደለም።

መጀመሪያ የወረደው የቁርኣን ምዕራፍ “አል-ዐለቅ” ነው። በአሁኑ ሰዐት የሚገኝበት ቅደም ተከተል ዘጠና ስድስተኛ (96) ነው። ሶሓባዎች የቁርኣን ምዕራፎችና አናቅጽ ቅደም ተከተ ሎችን ነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ባዋቀሩት መልኩ ጠንቅቀው ያውቁታል።

አሁን ባለንበት ሰዐት ተከበረው ቁርኣን በሠላሳ ክፍሎች (ጁዝእ)፣ እያንዳንዱ ክፍል ደግሞ በሁለት ንዑስ ክፍል (ሒዝብ)፣ እያንዳንዱ ንዑስ ክፍል ደግሞ በአራት ንዑስ ክፍሎች (ሩቡዕ) ተደራጅቶ ተዋቅሯል።

በዚህ መልኩ የተደራጀውና የተዋቀረው፣ ሙስሊሞች ቁርኣንን ሲያነብቡ ምቹና ቀላል እንዲ ሆንላቸው በሚል ዓላማ በቁርኣን ሊቃውንት ምሁራዊ ጥረት ነው።

### ስድስተኛ፡- ተከበረው ቁርኣንን መማር፡-

ሙስሊሞች ተከበረው ቁርኣን በነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ በወረደው መልኩ፣ በቃል በመሸምደድና አነባበቡን በመማሩ ረገድ ከፍተኛ የሆነ ትኩረት ሰጥተዋል።

ቁርኣንን በትክክልና በጥራት የሚያነብቡና የሚያዜሙ ሶሓባዎች ተከታዮቻቸው ተቢዕዮችን ይዘቱን በደንብ ጠንቅቀው እንዲያውቁ አድርገው የተከበረው ቁርኣንን በጥንቃቄ አስተምረዋቸዋል።

እያንዳንዱ አንቀጽ ዘንድ ቆመው በጥሞና መልእክቱን እንዲገነዘቡት አስችለዋቸዋል። ዕውቀትንም ተግባርንም በአንድ ላይ አዛምደው ተምረውታል። ከዚያም ቁርኣንን በቃላቸው የሸመደዱ (የሐፊዞ) ታቢዕዮች ቁርኣን የማስነበቢያ የትምህርት ማዕከል ገንብተዋል።

ማዕከሉን ሲገነቡ መሠረት ያደረጉት፣ ከሶሓባዎች የተማሩትን የቁርኣን አነባበብ፣ የቁርኣኑ ይዘት፣ የፊደላትና የቃላቱን ቁጥር፣ የምዕራፎቹና የአናቅጹ ቅደም ተከተል፣ ትክክለኛ የድምጽ አወጣጥ፣ አሳምሮና አስውቦ ማዜሙን ነው።

የተከበረው ቁርኣን በአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ላይ በወረደው መልኩ ትምህርቱ እየተሰጠ፣ በቃል እየተሸመደደ፣ በዜማ መልክ እየተነበበ፣ ተማሪው ቁርኣንን ጠንቅቆ ከሚያውቀው መምህሩ ቃል በቃል ጥርት ባለ የዐረብኛ ቋንቋ ከአፉ እየተቀበለው እስካለንበት ዘመን ደርሷል።

የተከበረው ቁርኣን ከነቢዩ ሙሐመድ (ሰ.ዐ.ወ) በቀጥታ ከተማሩት ሶሓባዎች ዕውቀቱን ከቀሰሙት ታቢዕዮች በተገኘው መልኩ በተለያዩ የአነባበብ ዓይነቶች በዜማ መልክ ይነበባል። የቃላትና የፊደላት ድምፁ በተለያየ መልኩ በዜማ መልክ ይነበባል።

ከእነዚህ የአነባበብ ዓይነቶች ውስጥ በዘመናችን ታዋቂ የሆነው አነባበብ ተማሪው ሐፍስ ኢብን ሱለይማን በዘገበው መልኩ የዓሲም አነባበብ፣ "ወርሽ" በሚል የሚታወቀው ተማሪው ዑስማን ቢን ሰዒድ በተዘገበው መልኩ የናፊዕ አነባበብ ናቸው። እንዲሁም አል-ዱሪይ፣ አቢ ዐምር አል-በስሪይን መሰረት አድርጎ የዘገበው፣ ቃሉን፣ ከናፊዕ የዘገበው የአነባበብ ዓይነቶች ይገኛሉ።

## ሰባተኛ፡- የተከበረው ቁርኣን መልእክት ትርጉም (ተፍሲር)

"ተፍሲር" ማለት የተከበረው ቁርኣንን መልእክት ግልጽ አድርጎ መተርጎም ማለት ነው። አንድ ቃል የሚከስተውን መልእክት ለማወቅ፣ የቃሉን ይዘት ቆም ብሎ ማጥናትና መመርመርን ይጠይቃል።

ኀያሉ አላህ የተከበረው ቁርኣን የሚያነብቡ ሰዎች የመልእክቱን ይዘትና ትርጓሜ በደንብ እንዲገነዘቡ በጥብቅ አሳስቧቸዋል። እንደዚህ አለ፡-

***"(ይህ) ወዳንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሐፍ ነው፤ አንቀጾቹን እንዲያስተነትኑና የአእምሮ ባለቤቶችም እንዲገሰጹ (አወረድነው)።" ሷድ፥29***

"እንዲያስተነትኑ" ማለት ትርጉሙን እንዲገነዘቡ እንዲረዱ ማለት ነው።

የአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ለሶሓባዎች ግልፅ ያልሆኑላቸው የቁርኣን መልእክቶችን ያብራሩላቸው ነበር። ይሁንና ግን በወቅቱ የነበራቸው ከፍተኛ የቋንቋ ችሎታና የተከበረው ቁርኣን ቃል ይወርድ የነበረውም በቋንቋቸው በመሆኑ ምክንያት በርካታ የተከበረው ቁርኣን መልእክቶች እንዲብራሩላቸው አይጠይቁም ነበር።

በሰው ዘንድ የተከበረው ቁርኣን መልእክቶች ትርጉም (ተፍሲር) የበለጠ አስፈላጊ ሆኖ የተገኘው ከሶሓባዎች በኋላ ዓመታት ካለፉ በኋላ ነበር።

ከአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ከሶሓባዎቻቸውና ከሶሓባዎቹ ተማሪዎች (ታቢዕዮች) የተገኙና የተነገሩ የተከበረው ቁርኣን ማብራሪያዎች፣ የተከበረው ቁርኣንን መልእክቶች በመተርጎሙና በማብራራቱ ረገድ እጅግ አስፈላጊ መሣሪያ ሆኖ ተገኘ።

ይህ ዓይነቱ የቁርኣን መልእክት ማብራሪያ “ተፍሲር አል-መእሱር” የሚል ስያሜ የተሰጠው ሲሆን፣ የተከበረው ቁርኣን መልእክቶችን በማብራራቱ ረገድ ዋንኛና ግንባር ቀደም መሣሪያ በመሆን ያገለግላል።

ይህ ዓይነቱ ማብራሪያ ዋንኛ መሣሪያ ሊሆን የቻለበት ምክንያትም የተከበረው ቁርኣን የመ ጀመሪያው ትውልድ አባላት ግንዛቤን ስለሚገልጽልን፣ ይህ ትውልድ ከፍተኛ የዐረብኛ ቋንቋ ችሎታ የነበረው በመሆኑ፣ እንዲሁም ተከበረው ቁርኣን ይወርድ በነበረበት ወቅት የነበሩ ትን ሁኔታዎችና ክስተቶችን በቅርበት የተመለከተና በቀጥታ የተሳተፈ ትውልድ በመሆኑ ምክንያት ነው።

## 1. የቁርኣን ትርጉም (የተፍሲር) ዓይነቶች፡-

የቁርኣን ትርጉም ሊቃውንት ትኩረት አድርገው ከሚሰሩበት የአተረጓጎም ሁኔታ አንጻር የተለያዩ የአተረጓጎም አቅጣጫዎችን ተከትለዋል። የተከበረው ቁርኣን ቋንቋዊ ገጽታ ላይ ትኩረት አድርገው የትርጉም ሥራ የሚሰሩ አሉ። እንደዚሁም በሕግጋት ጉዳዮች ላይ ትኩረት የሚያደርጉ፣ ታሪካዊ ክስተቶች ላይ አተኩረው የሚሠሩ፣ አይምሮአዊ ወይም ደግሞ በሥነ-ምግባር ጉዳዮች ላይ አጠንጥነው የቁርኣን ትርጉም ሥራ ላይ የተሰማሩ ሊቃውንት ተፈጠሩ።

ይህንኑ መሠረት በማድረግ የቁርኣን ትርጉም ሊቃውንት በሁለት ይከፈላሉ፡-

እነርሱም አንደኛ፡- ከአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ከሶሓባዎች እና ከሶሓባዎቹ ተማሪዎች የተገኙ ትርጓሜዎችን መሠረት አድርገው የሚተረጉሙ (አል-ተፍሲር ቢልመእሱር)፣

ሁለተኛ፡- ትክክለኛ በመሆን የዕውቀት መሠረታዊያን ላይ ቆመው የነጻ አስተያየትና የምር ምር ትርጓሜ ዘዴን የሚከተሉ ናቸው።

## 2. የተሻለው የትርጉም ዘዴና መስፈርቶች፡-

“አል-ተፍሲር ቢልመእሡር” ወይም ከአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ)፣ ከሶሓባዎችና ከሶሓባዎቹ ተማሪዎች የተገኙ ትርጓሜዎችን መሠረት አድርጎ የመተርጎሙ ዘዴ ከሁሉም የሚቀድምና ተመራጭ ነው።

ምክንያቱም ይህ ዓይነቱ የትርጓሜ ዘዴ ከአላህ መልክተኛ (ሰ.ዐ.ወ) ከሶሓባዎቹና ከሶሓባ ዎቹ ተማሪዎች የተገኘ በመሆኑ እነርሱም ቁርኣንን በመረዳቱና በመገንዘቡ ረገድ አቻ የሌላ ቸው ትውልድ በመሆኑ ምክንያት ነው።

በ“አል-ተፍሲር ቢልመእሱር” የተብራራው አናቅጽ አጥጋቢ ካልሆነና በሚገባው ሁኔታ ካል ተገለጸ፣ የቁርኣን ትርጉም ሊቅ የሚከተሉትን መስፈርቶች በማሟላት ነጻ አስተያየቱንና ምር ምሩን መሠረት አድርጎ ለመተርጎም ይችላል። እነርሱም፡-

1. የቁርኣን አናቅጽ በመተርጎሙ ረገድ በ “አል-ተፍሲር ቢልመእሱር” የተረጋገጡ እውነ ታዎች ላይ መመሥረትና እነዚህን እውነታዎች በሚቃረን መልኩ አናቅጹን አለመተር ጎም።
2. ከተከበረው ቁርኣን አጠቃላይ ዐውዳዊ ትርጉምና ከነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንና ማብራሪያ ጋር ስሙም ሆኖ መገኘት። ከዚህ ጥቅል ዐውዳዊ ትርጉም በተቃራኒ መጓዝ ለየትኛውም የቁ ርኣን ትርጉም ሊቅ የተገባ አይደለም።

ተከበረው ቁርኣን እርስ በእርሱ ስሙም ሆኖ እራሱን የሚገልጽ ሲሆን እርስ በእርሱ ከመጣረስና ከመጋጨት የጠራና የጸዳ ነው። የነቢዩ (ሰ.ዐ.ወ) ሱንናም በቁርኣን ውስጥ በጥቅሉ የተገለጸውን ቁም ነገር በዝርዝር የማብራራትና የመተርጎም ሚና ያለው እስ ተምሕሮት ነው።

3. ቃላት የሚከስቱትን መልእክት በመረዳቱ ረገድና የዓረፍተ ነገር አገነባብና አወቃቀር ሁኔታ እንዴት እንደሆነ በማወቁ ረገድ በዐረብኛ ቋንቋ ችሎታ ብቁ ሆኖ መገኘትን ይጠይቃል። የተከበረው ቁርኣን ቃል የተገለጸው በዐረብኛ ቋንቋ ነው። የቋንቋውን መሠረታዊያን ጠንቅቆ መረዳትና መገንዘብን ይጠይቃል።
4. አሻሚ ትርጉም ያላቸው አናቅጽን ግልጽና ፍንትው ያለ ትርጉም ያላቸው አናቅጽ ውስጥ ማካተት ያስፈልጋል።

   ተከበረው ቁርኣን እራሱን በራሱ የሚገልጽ፣ የሚያብራራ መጽሐፍ ነው። በጣም አመዛኙ የቁርኣን አናቅጽ መልእክቶቹ ግልጽና ፍንትው ያሉ ናቸው። እንደዚሁም የተወሰኑ፣ ለአንዳንዱ ሰው አሻሚ የሆኑንና ግልፅ ያልሆኑ መልእክቶች የሚከስቱ አናቅጽም አሉ።

   እነዚህ አሻሚ የሆኑ አናቅጽን ግልፅና ፍንትው ያሉ አናቅጽ ውስጥ በማካተት መልእክትና ትርጉማቸውን ለመገንዘብ ይቻላል። ኀያሉ አላህ እንደዚህ አለ፡-

   **"እርሱ ያ በአንተ ላይ መጽሐፉን ያወረደ ነው፤ ከርሱ (ከመጽሐፉ) ግልጽ የኾኑ አንቀጾች አሉ፤ እነርሱ የመጽሐፉ መሠረቶች ናቸው። ሌሎችም ተመሳሳዮች አሉ፤ እነዚያማ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ማሳሳትን ለመፈለግና ትችቱን ለመፈለግ ከርሱ የተመሳሰለውን ይከታተላሉ። (ትክክለኛ) ትርጉምና መልእክቱን አላህ ብቻ እንጅ ሌላ አያውቀውም። በዕውቀትም የጠለቁት በርሱ አምነናል፤ ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው ይላሉ። የአእምሮ ባለቤቶችም እንጅ (ሌላው) አይገሰጽም።" አሊ-ዒምራን፥ 7**

5. ፍጥረተ ዓለሙ (ዩኒቨርስ) የተወሱበት አናቅጽ በሚተረጎምበት ጊዜ በተጨባጭ ምርምር የተረጋገጡ ሳይንሳዊ እውነታዎችን ብቻ መከተል፣ በተከበረው ቁርኣን ላይ ተገቢ ያልሆነ ትርጉም ላለመጫን መጠንቀቅ ስለሚያስፈልግ፣ ያልተረጋገጡ ሳይንሳዊ አስተያየቶች ላይ ከመመሥረት መቆጠብ ያስፈልጋል።
6. ጥርት ካለው የኢስላም ምንጭ እና የአላህ ቃል ትርጉም ሊያራርቅ በሚችል ሁኔታ የተበላሹ የትርጓሜ ስልቶችን ከመከተል መታቀብም ያስፈልጋል።

   ሆን ብሎ ግልፅ መልእክቱን ለማዛባት፣ ወይም የዐረብኛ ቋንቋ ዕውቀት ባለመኖር ምክንያት ወይም ደግሞ የአላህን ቃል አጠራለሁ በሚል የተሳሳተ አረዳድ ምክንያት ከዐረብኛ ቋንቋ ሕግ መሠረታዊያን ውጪ ከሚያደርግ የትርጉም ስልት ከመከተል መጠንቀቅም ያስፈልጋል።

### ስምንተኛ፡- የተከበረው ቁርኣን ተአምር፡-

የ"ተአምር" (ኢዕጃዝ) ሸሪዐዊ ትርጉም በሰው ዐቅም ለመተግበር የማይቻል ተግባር ወይም ሐሳብ ወይም ድርጊት ማለት ነው። ተአምር (ሙዕጂዛ) ነቢያት እና መልክተኞች ከአላህ የተላኩ ለመሆናቸው ማሳያ የሚሆን በሰው ዐቅም ሊተገበር የማይችል ድርጊት ማለት ነው።

የበተከበረው ቁርኣን ውስጥ "ሙዕጂዛ" የሚል ቃል አልተጠቀሰም። ቁርኣን ተአምርን ለማመልከት የተጠቀመው "አል-አያ" ወይም "አል-ቡርሃን" እና የመሳሰሉ ቃላትን ነው።

የተከበረው ቁርኣን የጎያሉ አላህ ንግግር፣ የአላህ ቃል ነው። ይዘቱ የተሟላ ነው። አናቅጹ፣ ቃላቱ፣ አገነባቡ እጅግ በውበት የተሞላ ነው። ጎያሉ ቁርኣን የሰው ልጅን የሚገዳደር ተአምር ነው። አላህ እንደዚህ አለ፡-

**"አ.ለ.ረ (አሊፍ ላም ራ ይህ ቁርኣን) አንቀጾቹ በጥንካሬ የተሰካኩ፣ ከዚያም የተዘረዘሩ የኾነ መጽሐፍ ነው፤ ጥበበኛ ውስጠ ዐዋቂ ከኾነው ዘንድ (የተወረደ) ነው።" ሁድ፥ 1**

የመካ ጣዖታውያን የተለያዩ ሐሰቶችንና አሉባልታዎችን በመንዛት፣ የተከበረው ቁርኣን ምንጭ ላይ ጥርጣሬ በመፍጠር ሰዎች ከቁርኣን እንዲርቁ ሙከራ አድርገው ነበር።1

ጎያሉ አላህ ጣዖታውያኑ የተከበረው ቁርኣንን የመሰለ ዐሥር ምዕራፎች ወይም አንድ ምዕራፍ እንኳ እንዲያመጡ በመጠየቅ የሚገዳደር አናቅጽ አውርዷል። በቁርኣን ላይ ስለ ሚቀጥፉት ነገር እውነተኞች ከሆኑ ይህንን እንዲያደርጉ ጋበዛቸው። አልቻሉም። ምንም እንኳ የተከበረው ቁርኣን ቃል የተገለጸው በቋንቋቸው በዐረብኛ ቢሆንም መሰሉን ለማም ጣት ተስኗቸው ተሸነፉ።

**ከቁርኣን ጋር መፎካከር ወይም መሰሉን ለማምጣት የሚቻል ነገር አይደለም። ጎያሉ አላህ እንደዚህ ይላል፡-"በእውነትም (ሙሐመድ) ቀጣጠፈው ይላሉን? ይህ ከሆነ መሰሉን (አንዲት) ሱራ አምጡ፤ ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን ሁሉ (ረዳት) ጥሩ፤ እውነተኞች እንደኾናችሁ (ተጋግዛችሁ አምጡ) በላቸው።" ዩኑስ፥38**

የተከበረው ቁርኣን ግልጽና ፍንትው ባለ ሁኔታ፣ የሰው ልጅም ሆነ ኢጋንንት በጠቅላላው ተሰባስቦ ቢተባበር እንኳ የተከበረው ቁርኣንን የሚመስል ቃል ከቶውንም ሊያመጡ እንደማ ይችሉ አስረግጦ ተናግሯል። ጎያሉ አላህ እንደዚህ አለ፡-

**"ሰዎችም ጋኔኖችም የዚህን ቁርኣን ብጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢኾንም እንኳ ብጤውን አያመጡም በላቸው።" አል-ኢስራእ ፥88**

የተከበረው ቁርኣን የፍጥረታት ቃል የማይመስለው የጎያሉ አላህ ንግግር የሆነ ተአምር ነው። ቁርኣን ቃላቱ፣ አናቅጹ፣ ቋንቋውና ግዙፍ የሆነው እጅግ ጥዑም ለዛ የተላበሰው የአገላለጽ ውበቱ፣ በውስጡ ያሉት እውነተኛ ታሪኮች፣ ሕግጋቱና ድንጋጌዎቹ፣ በነፍስና በሥነ-ልቡና ላይ ተፅዕኖ የመፍጠር ጎያልነቱ፣ በውስጡ ያካተታቸው ተጨባጭ እውነታ ዎች በሙሉ ተአምራት ናቸው።

የተከበረው ቁርኣን ስንትና ስንት የፊዚክስ፣ የሥነ-ፈለክ፣ የሥነ-ሕይወት፣ የሕክምና እና ሌሎች ሊቃውንትን አስደንቋል፣ አስደምሟል።

ከአንድ ማንበብና መጻፍ ከማይችል ነቢይ፣ የማይጽፉና የማያነቡ ሕዝብና ምንም መሰል ዕውቀት ከሌለው አካባቢ ሊመነጩ የማይችሉና የተከበረው ቁርኣን በውስጡ የሚያወሳ ቸው ተጨባጭ ዕውቀቶች፣ ፍጥረተ-ዓለሙ ውስጥ ስላሉ ምስጢራዊ ነገሮች የሚሰጠው ጥቆማዎች፤ በዘርፉ ለተሰማሩ በርካታ ሊቃውንት መስለም ሰበብ ለመሆን ችሏል። ምክ ንያቱም እነዚህን መሰል በሳይንሳዊ ምርምር ብቻ ሊደርስባቸው የማይችሉና በተከበረው ቁርኣን ውስጥ የተጠቀሱ እውነታዎች የሰው ንግግር ሊሆን እንደማይችልና የንግግሩ ባለቤት የሰውና የፍጥረተ -ዓለሙ ፈጣሪ መሆኑን በማወቃቸው ነው።

1 በዚህ ጉዳይ አል-አንዓም፡7 ፥ 25 /አል-አንቢያእ፡ 5 / ሰበእ፡ 43 / ዩኑስ፡ 69/ አል-ሷፋት፡ 36/ ሷድ፡ 4/ አል-ጡር፡ 30 የተጠቀሰውን ተመልከቱ

በተከበረው ቁርኣን ውስጥ የጎያሉ አላህን ብቸኛ ፈጣሪነትና አስገኚነት የሚያወሱ በርካታ አናቅጽ ሰፍረዋል። ጎያሉ አላህ እንደዚህ ይላል:-

**“እርሱም (ቁርኣን) እውነት መሆኑ ለነርሱ እስከሚገለጽላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ታምራቶቻችንን በእርግጥ እናሳያቸዋለን፤ ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ መኾኑ አይበቃቸውምን?” ፉሲለት፥53**

**ዘጠነኛ:- የተከበረው ቁርኣን መልእክቶች ትርጉም:-**

ትርጉም ማለት በአንድ ቋንቋ የተነገረን ቃል ወደ ሌላ ቋንቋ መመለስ ማለት ነው። የትርጉም ሥራ በጣም ከባድ ነው። ጽሑፍን ከሚገነቡ ነገሮች ውስጥ አንዱ ቋንቋዊ አገላለጽ ነው። በአንድ ቋንቋዊ አገላለጽ የተቀመረን ጽሑፍ እንዳለ ወስደን ከነ ሙሉ መልእክቱ ወደሌላ ቋንቋ መተርጎም ከባድ ሥራ የሚጠይቅ ተግባር ነው።

የሰው ሥራ ውጤት የሆነን ጽሑፍ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጎም በዚህ መልኩ ከባድ ከሆነ የአላህ ቃል የሆነውን ተከበረው ቁርኣን በሌላ ቋንቋ መተርጎም ደግሞ የበለጠ ከባድ መሆኑ አያጠያይቅም።

የተከበረው ቁርኣን በዐረበኛ ቋንቋ ከጎያሉ አላህ የወረደ የአላህ ንግግር ነው። ንግግሩም ሆነ መልእክቱ ከጎያሉ አላህ በወሕይ የተገለጸ የርሱ ቃል ነው።

የዐረብኛውን የተከበረው ቁርኣን ምሉእ ትርጓሜ ወደ ሌላ ቋንቋ እንዳለ መተርጎም ለአንድ ሰው በቀላሉ የሚሆን አይደለም። ወይም የዐረብኛው አገላለጽ በውስጡ የያዘውን ሙሉ ውበት እንዳለ ወደ ሌላ ቋንቋ መተርጎም የሚቻል አይደለም።

ምንም እንኳ የተከበረው ቁርኣንን መተርጎም በዚህ መልኩ ከባድ ቢሆንም፣ የኢስላም ሊቃ ውንት ግን ተከበረው ቁርኣንና መልእክቱን ሁሉንም ዓይነት ቋንቋዎች ለሚናገረው የዓለማ ችን ሕዝብ ማድረስ አስፈላጊ ተግባር መሆኑን በአጽንዖት ይናገራሉ። ይህ ደግሞ በትርጉም ካልሆነ በስተቀር ሊሳካ አይችልም።

የተከበረው ቁርኣንን ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎም:-

1. የተከበረው ቁርኣን መልእክቶቹን መተርጎም ማለት የቁርኣኑ ይዘት የሚያስተላልፈውን መልእክት በመግለጽ ብቻ የሚገገታና ተፍሲር ያልሆነ ትርጓሜ ማለት ነው።
2. ወይም ደግሞ ለቁርኣኑ ይዘት የትንታኔ ትርጉም (ተፍሲር) በመስጠት በገለጻና በማብራ ሪያ ላይ በመመሥረት መተርጎም ሊሆን ይችላል። ይህ ዓይነቱ አሠራር ከዓረብኛ ቋንቋ ውጪ የሆነ የቁርኣን ተፍሲር ሥራ ሊባል ይችላል።

ሆኖም ግን የቱንም ያክል በጥንቃቄ ላይ ሆነን ተከበረው ቁርኣንን ወደሌላ ቋንቋ ብንተረጉ መው፣ ተርጓሚው የቱንም ያክል በዐረብኛም ሆነ በሚተረጉምበት ቋንቋ ብቁ ቢሆን እንዲ ሁም የፈለገውን ያክል የቁርኣንን መልእክት ይረዳ፣ ያ ወደ ሌላ ቋንቋ የተተረጎመው ጽሑፍ ግን በምንም ዓይነት “ቁርኣን” ነው ሊባል አይችልም። በሁለት ምክንያቶች:-

አንደኛ:- በመሠረቱ የተከበረው ቁርኣን በዐረብኛ ቋንቋ የወረደ በከፍተኛ ሁኔታ ግልጽ፣ ፍንትው ያለ የጎያሉ አላህ ንግግር በመሆኑ፣ የአናቅጹን ይዘት ዐረብኛ ባልሆነ ሌላ ቋንቋ መተርጎሙ፣ የተተረጎመውን ቃል “ቁርኣን ነው” ከመሰኘት ውድቅ ያደርገዋል።

ሁለተኛ:- የትርጉም ሥራ የሚያመለክተው ተርጓሚው ለቁርኣን መልእክቶች ያለውን ግንዛቤ ነው። ይህ አሠራር ከተፍሲር ጋር ተመሳሳይነት ያለው ነገር ነው። የዐረብኛ ተፍሲር እንኳ “ቁርኣን” ነው ሊባል እንደማይቻለው ሁሉ፣ ወደ ሌላ ቋንቋ የተመለሰ ትርጉምም “ቁርኣን” ነው ልንለው አንችልም።

የተከበረው ቁርኣን መልእክቶች ትርጉም ተቀባይነት ያለው እንዲሆን ከተፈለገ፣ የተከበ ረው ቁርኣንን መልእክቶች በመግለጹ ረገድ የዘርፉ ሊቃውንት ያኖሯቸውን መስፈርቶች አሟልቶ መገኘትን ይጠይቃል። እንደዚሁም ተርጓሚው በትርጉሙ አማካኝነት የተዛባ የቁርኣን ትርጉም ለማስተላለፍ የሚፈልጉ፣ የኢስላምን ገጽታ ለማጠልሸት የሚሹ ወገኖች መሣሪያ እንዳይሆን ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

እንደዚህ ያለው ሁኔታ ሆን ብለው ኢስላምን ለማጥፋት በተነሱ ኦሬንታሊስቶችና ሙስሊም ሳይሆኑ ሙስሊም መስለው በሰረጉ ኀይሎች በተተረጎሙ በርካታ የትርጉም ሥራዎች ላይ ተስተውሏል። እነዚህ ኀይሎች ታላቁን የኢስላም ሃይማኖት ለመናድና ንጹሕ የሆነው እም ነቱን ለማደፍረስ የተበላሸ እምነት አንግበው በመስረግ ሙከራዎችን አድርገዋል።

ጥርት ያለው የተከበረው ቁርኣንን መልእክት የዐረብኛ ቋንቋ ለማይናገሩ የዓለማችን ሕዝቦች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ለማድረስ የሚል የተቀደሰ ዓላማ በማንገብ፣ በመዲነቱል ሙነወራ ከተማ የሚገኘው የንጉሥ ፈህድ የተከበረው ቁርኣን ኅትመት ተቋም፣ ተአማኒነት ያላቸው የተከበረው ቁርኣን ትርጉሞችን ለማተም ኀላፊነቱን ተሸክሟል።

ምስጋና የዓለማት ጌታ ለሆነው አላህ የተገባ ነው። የአላህ እዝነት፣ ሰላምና በረከት በነ ቢያችን ሙሐመድ፣ በቤተሰቦቻቸውም፣ በሶሓባዎቻቸውም፣ በሶሓባዎቻቸው ተማሪዎች እና የእነርሱን ጎዳና እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ በመልካም በተከተሏቸው ላይ ሁሉ ይሁን። አሚን።

## الاستعاذة

**አል ኢስቲዓዛ (በአላህ ብቻ ከሰይጣን መጠበቅ)**

(አዑዙ ቢላሂ ሚነ ሸይጧኒ ረጂም) ትርጉም፡- ከተረገመው ሰይጣን ተንኮል በአላህ ብቻ እጠበቃለሁ። (አዑዙ ቢላሂ ሚነሽ-ሸይጣኒ ር-ረጂም) የሚለው የዱዓ ቃል እንጂ የፋቲሓህ አካል አይደለም። ስለሆነም ከቁርአን ጋር አልተፃፈም። ሆኖም ግን ማንም ቁርኣንን ለማንበብ ሲያስብ በእሱ መጀመሩ ተገቢ ነው። ይህን አስመልክቶ ቁርኣን እንዲህ ይላል፡-«ቁርኣንን ለማንበብ ባሰብክ ጊዜ እርጉም ከሆነው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ» (የንቧ-ምዕራፍ፡ 98)

እናም ሰይጣን ከጂኖችም እንዳለ ሁሉ ከሰዎችም መካከል ይገኛል። ከቶዉንም የሰው ሰይጣን በጣም አደገኛ ነው። ይህንን አባባል ቁርኣን ሲያረጋግጥ «ከአጋንንቶችም ሆነ ከሰዎች ሰይጣናት እጠበቃለሁ በል» (የሰዎች- ምእራፍ፡ 6) በማለት ያዛል።

ሰይጣን የትክክለኛ አማኞች እውቅ ጠላት እንደሆነና እሱን አጥብቀን መጠንቀቅ እንዳለብን «ሰዎች ሆይ! በምድር ካለው ነገር የተፈቀደና ጤናማ የሆነን ምግብ ብሉ የሰይጣንንም ዱካ አትከተሉ እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና። እርሱ የሚያዛችሁ በኃጢአትና በፀያፍ ነገር በአላህ ላይ የማታውቁትን እንድትናገሩ ነውና»

(የላሟ ምዕራፍ፡ 168-169)

«እናንተ ያመናችሁ ሆይ! ሁላችሁም ለአላህ እጅ ስጡ። የሰይጣንን እርምጃዎች አትከተሉ፡ እርሱም ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና» (የላሟ- ምዕራፍ፡ 208)

# ምዕራፍ (1)
# የመክፈቻይቱ ምዕራፍ
# (ሱረቱ አል-ፋቲሐህ)

سُورَةُ الفَاتِحَةِ

## የአንቀፆቹ ብዛት (7) ናቸው። የወረደው በመካ ነው።

## የመክፈቻው ምእራፍ መግቢያ

አቡ ሰዒድ አልሙዓላ እንዳስተላለፉት፡- ከዕለታት አንድ ቀን መስጂድ ውስጥ እየሰገድኩኝ ሳለሁ የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ ጠሩኝ። እኔ ግን ለጥሪያቸው መልስ አልሰጠሁም ነበር። ከዚያ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ!እየሰገድኩ ስለነበር ነው አልኳቸው። እሳቸውም፡- «እንዴ አላህ «መልዕክተኛው ሕያው ወደሚያደርጋችሁ እምነት በጠራችሁ ጊዜ፤ ለአላህና ለመልእክተኛው ታዘዙ። አላለምን?» ካሉኝ በኋላ «ከዚህ መስጅድ ሳትወጣ በፊት ከቁርኣን ውስጥ በጣም ትልቅ የሆነውን ምዕራፍ አስተምርሃለሁ»ብለው እጄን ያዙኝ። መስጅድ ሊወጡ ሲሉ «ከቁርኣን ውስጥ በጣም ትልቁን ምዕራፍ አስተምርሃለሁ። አላሉኝም ነበር?» በማለት ጠየቅኳቸው። እሳቸውም «አል-ሐምዱሊላሂ ረብቢል-ዓለሚይን የሚለው የፋቲሐህ ምዕራፍ ነው። ይህ ምዕራፍ ከቁርኣን ውስጥ ታላቅ ስፍራ የተሰጠው ነው» አሉኝ። ይህ ታላቅ የቁርኣን ምዕራፍ በተከበረው ቅዱስ ቁርኣን አቀማመጥ ቅደም ተከተል መሰረት በመጀመሪያው ረድፍ ላይ ይገኛል። በዚህም ምክኒያት ነው ይህን ስያሜ ያገኘው። እናም የምዕራፉ አናቅፅ ሰባት ናቸው። ከመልዕክታቸው አንፃርም ለሁለት ይከፈላሉ። የመጀመሪያዎቹ ግማሽ አናቅፅ ስለ አላህ ትልቅነት፤ ብቸኛ አምላክነት፤ እርዳታም ሆነ እገዛ መጠየቅ የሚገባው ከእሱ ብቻ መሆኑን የሚያወሱ ሲሆኑ፤ ቀሪዎቹ ደግሞ ስለ ሰው ልጅ የሚያወሱ ናቸው።

የምዕራፉ ዋና ትኩረት ያደረገበት በተሟላ መልኩ የአምልኮ ተግባርን ለአላህ ብቻ ማድረግን ነው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ١

**1.** በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)።*

* «ቢስሚላሂ አር-ረሕማኒ አር-ረሒሂም» ኢብኑ ዐባስ እንደዘገቡት፡- ነብዩ የአንድን ምዕራፍ ማብቃት ያውቁት የነበረው «ቢስሚላሂ አር-ረሕማኒ አር-ረሒሂም» ሲወርድ ነበር» ብለዋል። አቡዳውድ እንደዘገቡትም ዐብዱላህ ብን መስዑድ፡- «በሁለት ምዕራፎች መካከል መለያ ማወቅ የጀመርነው «ቢስሚላ አር-ረሕማኒ አር-ረሂሒም» ከወረደ ወዲህ ነው» ብለዋል። ዐብዱላህ ብን ዑመር፡- «ቢስሚላሂ አር-ረሕማኒ አር-ረሒሂም» ከሁሉም ምዕራፍ ጋር አብሮ ወርዷል» ብለዋል። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ٣ مَٰلِكِ يَوۡمِ ٱلدِّينِ ٤

**2-4.** ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ፤ ለሆነው ይገባው እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ ለሆነው። የፍርዱ ቀን ባለቤት ለሆነው።(ለአላህ ብቻ ይገባው)።

إِيَّاكَ نَعْبُدُ وَإِيَّاكَ نَسْتَعِينُ ۝٥ ٱهْدِنَا ٱلصِّرَٰطَ ٱلْمُسْتَقِيمَ ۝٦
صِرَٰطَ ٱلَّذِينَ أَنْعَمْتَ عَلَيْهِمْ غَيْرِ ٱلْمَغْضُوبِ عَلَيْهِمْ وَلَا ٱلضَّآلِّينَ ۝٧

5-7. (ሙስሊሞች ሆይ! ጌታችን ሆይ!) አንተን ብቻ እንገዛለን። ከአንተም ብቻ እርዳታን እንለምናለን። ቀጥተኛውን መንገድ ምራን። የእነዚያን ለእነርሱ በጎ የዋልክላቸውን፤ በእነርሱ ላይ ያልተቆጣህባቸውንና ያልተሳሳቱትንም ሰዎች መንገድ (ምራን በሉ)።*

✳ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ኣሚን (ዱዓችንን ተቀበለን) የሚለዉን ቃል ማንበብ ተገቢ ነው። አህመድና ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ)፡- «አይሁዶች በሰላታችሁና ኣሚን በማለታችሁ የተመቀኟችሁን ያህል በምንም ነገር አልተመቀኟችሁም» ብለዋል። ትርጉሙም ዱዓችንን ተቀበለን ማለት ነው። ኢማምም የሆነ ሰው ቢሆን በትክክለኛው አባባል ፋቲሃን አንብቦ ሲያበቃ ድምፁን ከፍ አድርጎ ማንበብ ተገቢ መሆኑን ዋኢል ብን ሁጅር የተባሉት ሱሃቢ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) (ወለዷሊን) የሚለዉን ካነበቡ በኋላ ድምፃቸዉን ከፍ አድርገው ኣሚን የሚለዉን ሳብ በማድረግ ያነቡት ነበር ብለዋል። ብቻዉን ሰጋጅና ተከታይ የሆነ ሰው በሁሉም ዘንድ ማለቱ ተገቢ ነው።

**ከመክፈቻው ምዕራፍ ከምናገኛቸው ዋና ዋና ነጥቦች መካከል በጥቂቱ፡-**

1. ምስጋና በሙሉ የሚገባው የሁለንተናዊው ዓለም ፈጣሪና ተንከባካቢ ለሆነው ለአላህ ብቻ እንደሆነ፤
2. አላህ የሰው ልጆች በምድራዊ ቆይታቸው በሰሩት ምንዳ በሚያገኙበት የትንሳኤ ቀን ብቸኛ ፍርድ ሰጪ ጌታ መሆኑን፤
3. ከዱዓ ስርዓቶች መካከል ቅድሚያ አላህን ማሞገስ መሆኑን፤
4. ለምድራዊም ሆነ አኼራዊ ጉዳዩች ብቸኛው ተለማኝ አንድ አላህ ብቻ እንደሆነ፤ ከርሱም በስተቀር ሊመለክና እርዳታ ሊጠየቅ የሚችል ሌላ አካል እንደሌለና በፍፁምነት ለእሱ መተናነስና እርሱን ብቻ መጠየቅ እንደሚገባ፤
5. አላህ መልካም ስሞችና ንፁህ ባህሪያት እንዳሉት እና ከባህሪያቶቹም እጅግ በጣም አዛኝና ሩህሩህ የሚለው መሆኑን፤
6. ቀጥተኛ መንገድ የነብያትና ፈለጋቸዉን የተከተሉ ሁሉ የተጓዙበት በመሆኑ የእነርሱን አርአያነት መከተል እንደሚገባን፤
7. የአላህ ቁጣ ያደረባቸውን ሰዎች መንገድ ከመከተል መታቀብ ግዴታ መሆኑንና ለዚህም የአላህ እገዛ አስፈላጊ እንደሆነ ና ሁሌም የእሱን እገዛ መጠየቅ እንደሚያስፈልግ፤
8. ማንም ሰው ዱዓ ከማድረጉ በፊት አላህን ማመስገን፤ ማወደስና በኸይር ስራው መወሰን ተገቢ መሆኑ፤
9. ወደ ቅኑዉም ሆነ መጥፎው መምራት የአላህ ስልጣን በመሆኑ ወደ ቅኑዉ እንዲመራን እሱን ብቻ እንለምናለን፤
10. ሰዎች ቅኑን መንገድ ለመከተልም ሆነ ለመጥመም ያላቸው ሚና ምክንያቶችን ማመቻቸት፤
11. ከአላህ ሌላ ያለን አካል ነብያትንም ሆነ ወሊዮችን እርዳታ መጠየቅ ተገቢ አለመሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የመክፈቻው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (2)
## የላሟ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-በቀረህ)

سُورَةُ البَقَرَةِ

### የወረደው በመዲና ነው። የአናቅፁ ብዛት (286) ናቸው።
### የሱረቱ አል በቀራህ መግቢያ

የላሟ ምዕራፍ ከቁርኣን ምራፎች ሁሉ ረጂሙ ነው። ከቁርኣን ምእራፎች ሁሉ አጭሩ ደግሞ የአል-ከውሰር ምዕራፍ ነው። ከቁርኣን አናቅፅ ሁሉ ረጂሙ በዚሁ ምዕራፍ ዉሥጥ ያለው የመበዳደር ህግ አንቀፅ ሲሆን፤ አጭሩ ደግሞ «ወዱሃ» «ወልፈጅሪ» «ወል ዐስሪ». የሚሉት አናቅፅ ናቸው።

ምዕራፉ እንደ ሌሎች በመዲና የወረዱ ምእራፎች ሁሉ ከተውሒድ ይልቅ በህግጋት ላይ ሰፋ ያለ ገለፃ ይሰጣል። ሆኖም ስለ ትክክለኛው ዐቂዳ መሰረቶች በተደጋጋሚ ጥሪ ያደርጋል። ከተቃራኒው ማለትም፡- ከሺርክ፤ ከክህደት በተለይ ከንፍቅና ህዝቦችን በሰፊው ያስጠነቅቃል።

ምዕራፉ የሚጀምረው ሶስቱን የሰው ልጅ አይነቶችን ማለትም፡- የአማኞችን፤ የከሓዲያንንና የአስመሳዮችን ባህሪ በሰፊው በመግለፅ ነው። የአባታችን አደምንና የኢብሊስን፤ የአባታችን አደምንና የእናታችን ሐዋን ታሪክ፤ የእስራኤላዊያንን ሰፊ ታሪክ፤ የሙሳንና የላሚቱን ታሪክ በይፋ ይዘግባል። የሶላትን፤ የዘካን፤ የፆምን፤ የዱዓን፤ የሐጅን፤ የጦርነትን ህግጋትና የቂሷስን እርምጃ ህግ፤ በአላህ ዲን ላይ ገንዘብን ማውጣት ከፍተኛ አጅር እንዳለው፤ ሥነ ምግባር ነክ ጉዳዮችን፤ የእውነተኝነትን ትልቅነት፤ የውሸትን አስከፊነት፤ የክህደትን አስቀያሚነት፤ ማህበራዊ ጉዳዩችን ጋብቻን፤ ፍችን፤ የዒዳን አይነቶችና አቆጣጠራቸውን፤ ልጅ ማጥባትን፤የአጥቢ ቀለብን፤ መሸጥና መግዛትን፤ የወለድን አስከፊነት፤ የብድርን ስርአት እና ሌሎችንም ህግጋት አካቷል። አማናን መጠበቅ ግዴታ መሆኑን፤ ምስክርን መደበቅ ክልክል መሆኑንም እንዲሁ በይኗል።

ምዕራፉ በመዲና በመጀመሪያ አካባቢ ከወረዱ ምእራፎች አንዱ ከመሆኑም በላይ አንሷሮች ልዩ ትኩረት ይሰጡት የነበረ ምዕራፍ ነው። ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር ይህን ምዕራፍ ብቻ እየተማሩ ስምንት አመታትን እንዳሳለፉበት መናገራቸውን ኢማሙ ማሊክ ሙወጦእ በተባለው መፅሐፋቸው ላይ ዘግበዋል። አብዛኛዎቹ የዚህ ምዕራፍ አናቅፅ ነብዩ (ﷺ) ወዲያው ወደ መዲና እንደሄዱ የወረዱ ሲሆኑ (281) ኛው አንቀፅ ግን በብዙሃን ምሁራን ዘንድ ከጠቅላላው የቁርኣን አናቅፅ መካከል ለመጨረሻ ጊዜ የወረደ ነው ተብሏል። ምዕራፉ ሁላችንም ሁል ጊዜ ልንረሳው የማይገባንን ዱዓ በማስተማር መልዕክቱን ያጠቃልላል።

በአጠቃላይ የምዕራፉ ዋና ትኩረት

1. ሰዎችን ለምድር ልማትና ዲንን ለመሸከም ማዘጋጀት፤
2. የሰዎች አይነትም ስንት እንደሆነ መተንተን፤
3. የእምነት መሰረቶችና የሸሪዓ ህግጋትን መተንተን፤
4. ምዕራፉ የተሰየመበት የላሟን ታሪክ መዘርዘር፤
5. እና ሌሎችንም ማስተማር ነው።

የምዕራፉ መጀመሪያው አነባበቡን በተመለከተ «አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም» ተብሎ ነው የሚነበበው።

ሌሎችም እንደዚሁ በፊደላት የተጀመሩት ምእራፎች ሁሉ እንዲሁ በፊደሉ ስም ነው የሚነበቡት።

የላሟ ምዕራፍ ሲባል የላሟ ታሪክ በሰፊው የሚዘገብበት ምዕራፍ ማለት ነው እንጂ በምዕራፉ ዉስጥ ሌላ ጉዳይ አልተወሳበትም ማለት እንዳልሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

ጦበራኒ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) «ለሁሉም ነገር ጉልላት አለው። የቁርኣን ጉልላቱ ግን የላሟ ምዕራፍ ነው። በሌሊት ያነበበው ሰው ሶስት ሌሊት ሙሉ ሰይጣን እቤቱ ዉስጥ አይገባም። በቀን ያነበበው ሰውም ሶስት ቀን ሙሉ ሰይጣን እቤቱ አይገባም» ብለዋል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓ ﴿١﴾

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም፤*

✷ በአነዚህና በመሰል ፊደላት የተጀመሩ ምዕራፎች 29 ናቸው። ሆኖም በእነሱ ምን እንደፈለገ አላህ ብቻ በትክክል ያውቀዋል። በብዙ ዐሊሞች ዘንድ የተመረጠው ከእነዚህና ከመሰል ፊደላት የተዋቀረው የቁርኣንን አሸናፊነትና ተአምር ለመጠቆም ነው የሚለው አባባል ነው። ይህንን አባባል ከሚያጠናክሩ ነገሮች በብዛት ከፊደላቱ ቀጥለው የሚመጡት አናቅፅ ስለ ቁርኣን መሆኑ ነው።
ኢብኑ ከሲር እንዳሉት:-
እነዚህ የተቆራረጡ የቁርአን ፊደላቶች ከየምዕራፎች መጀመሪያ መደረጋቸው የቁርአንን ተአምራዊነት ሙዕጅዛ ያመለክታል ቁርአን የተገነባው ከነዚህና መሰል የአረብኛ ፊደላት ነው።
የሰውም ልጅ እነዚህን ፊደላት በመጠቀም አንድ አንቀጽ እንኳ ማምጣት እንደማይችል ያመለክታል ይህ ደግሞ የቁርአንን ታላቅ ተአምራዊነት ያመለክታል።

ذَٰلِكَ ٱلۡكِتَٰبُ لَا رَيۡبَۛ فِيهِۛ هُدٗى لِّلۡمُتَّقِينَ ﴿٢﴾ ٱلَّذِينَ يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡغَيۡبِ وَيُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ
وَمِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ يُنفِقُونَ ﴿٣﴾ وَٱلَّذِينَ يُؤۡمِنُونَ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبۡلِكَ وَبِٱلۡأٓخِرَةِ
هُمۡ يُوقِنُونَ ﴿٤﴾ أُوْلَٰٓئِكَ عَلَىٰ هُدٗى مِّن رَّبِّهِمۡۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ﴿٥﴾

**2-5.** ይህ ታላቅ መፅሐፍ (ቁርኣን) (ከአላህ የተወረደ ለመሆኑ) ምንም ጥርጥር የለበትም። አላህን ለሚፈሩ፤ መመሪያ ነው ለእነዚያ በሩቅ ነገር ለሚያምኑ፤ ሶላትን ደንቡን ጠብቀው ለሚሰግዱ፤ ከሰጠናቸውም ሲሳይ ለሚቸሩ፤ (መልክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነዚያም ወደ አንተ በተወረደው መፅሐፍና ከአንተ በፊትም በተወረዱት መፅሐፍት ለሚያምኑ፤ በመጨረሻውም ቀን መኖር (እና ከእሱ ጋር በተያያዙት ነገሮች ሁሉ) ለሚያረጋግጡ ሰዎች ሁሉ (መመሪያ ነው)። እነዚያ (የተጠቀሱትን ባህሪያት የሚላበሱ ሰዎች ሁሉ) በጌታቸው መመሪያ ላይ የሚጓዙ ናቸው። ፍላጎታቸውንም ያገኙትም እነርሱ ብቻ ናቸው።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከትክክለኛ አማኞች ባህሪያት መካከል አምስቱን መግለፅ፤
2. የቁርኣንን ትልቅነትና በቁርኣን የተጠቀሱት መጽሐፍት፤ ተውራት፤ ዘቡር፤ ኢንጅልና ቁርኣን ከአላህ እንደወረዱ መጠቆም፤
3. እነዚህ መፅሐፍት ከተስማሙባቸው ጉዳዮች መካከል ዋናው የአላህን ብቸኛ አምላክነት መሆኑን፤
4. ከቁርኣን በፊት የነበሩት መፃሕፍት መልዕክት ሁሉ ብዙ ቦታ የተለዋወጠና አንዳንዱም እስከ መጨረሻው እንደጠፋ ስለሚታወቅ ከአላህ በወረደው ብቻ ማመን እንዳለብን፤
5. አማኞች ሁለት አይነት ማለትም ጠንካራ አማኞችና ተራ አማኞች መኖራቸዉን እንማራለን።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ سَوَآءٌ عَلَيۡهِمۡ ءَأَنذَرۡتَهُمۡ أَمۡ لَمۡ تُنذِرۡهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ٦
خَتَمَ ٱللَّهُ عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ وَعَلَىٰ سَمۡعِهِمۡۖ وَعَلَىٰٓ أَبۡصَٰرِهِمۡ غِشَٰوَةٞۖ وَلَهُمۡ عَذَابٌ عَظِيمٞ ٧

**6-7.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ (ብቸኛ አምላክነት፣ በአንተ መልዕክተኛነትና በአላህ አንቀፆች) የካዱ ሰዎች ሁሉ ብታስጠነቅቃቸውም ባታስጠነቅቃቸውም ለእነርሱ ሁሉም እኩል ነው። (ምንም ለውጥ አያመጣም) አያምኑምና። አላህ (እነዚያ እውነትን እያወቁ የካዱ ሰዎችን) በልቦቻቸው ላይና በመስሚያቸው ላይ አትሞባቸዋል። በዓይኖቻቸው ላይም መሸፈኛ አለ። ለእነርሱም በሲኦል ውስጥ ከባድ ቅጣት አለባቸው።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (6-7) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከከሓዲያን ተግባራት መካከል ዋናው ተነግሮ አለመስማት መሆኑን መጠቆም፤
2. ከሓዲያን እያዋከቧቸው የነበሩትን ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) እና ባልደረቦቻቸዉን ማፅናናት፤
3. የአላህ ቅጣት የተረጋገጠባቸው ሰዎች አስተማሪው ምንም ጠንካራ ቢሆን እንኳን በአላህ እንደማያምኑ፤
4. ምክር ሲሰጠው ስጋት የማይታይበት ግትር ሰው የአላህን ምክር ከማይቀበሉት ከሓዲያን ጋር ተመሳሳይነት እንዳለው፤
5. መስማትና ማየት እውነትን ለመረዳት ከሚያስችሉ መንገዶች ዋና ዋናዎች መሆናቸውን፤
6. ከሃዲያን ሁለት አይነት ማለትም አቀንቃኞችና ተከታዮች መሆናቸዉን እንማራለን።

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَبِٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَمَا هُم بِمُؤۡمِنِينَ ٨ يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ
وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَمَا يَخۡدَعُونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمۡ وَمَا يَشۡعُرُونَ ٩ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٞ فَزَادَهُمُ ٱللَّهُ
مَرَضٗاۖ وَلَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمُۢ بِمَا كَانُواْ يَكۡذِبُونَ ١٠

**8-10.** ከሰዎች መካከል ለይስሙላ በአላህና በመጨረሻው ቀን አምነናል የሚሉ ክፍሎች አሉ። እነርሱ ግን (የሚዋሹ እንጅ) ትክክለኛ አማኞች አይደሉም። አላህንና እነዚያን በትክክል በአላህ ያመኑትን ሰዎች ያታልላሉ። ነገር ግን በዚህ ተግባራቸው ነፍሶቻቸውን እንጂ ሌላን ማንንም አያታልሉም። እነርሱ ግን ይህ መሆኑን በትክክል አያውቁም። በልቦቻቸው ውስጥ (የንፍቅና) በሽታ ሰርጿል። አላህም ሌላን በሽታ ጨመረባቸው። ለእነርሱም ይዋሹ በነበሩበት ምክንያት አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ لَا تُفْسِدُواْ فِي ٱلْأَرْضِ قَالُوٓاْ إِنَّمَا نَحْنُ مُصْلِحُونَ ١١ أَلَآ إِنَّهُمْ هُمُ ٱلْمُفْسِدُونَ وَلَٰكِن لَّا يَشْعُرُونَ ١٢ وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ ءَامِنُواْ كَمَآ ءَامَنَ ٱلنَّاسُ قَالُوٓاْ أَنُؤْمِنُ كَمَآ ءَامَنَ ٱلسُّفَهَآءُۗ أَلَآ إِنَّهُمْ هُمُ ٱلسُّفَهَآءُ وَلَٰكِن لَّا يَعْلَمُونَ ١٣

**11-13.** ለእነርሱም በምድር ላይ ሁከትን አትፍጠሩ በተባሉ ጊዜ እኛ እኮ አቅኚዎች ነን ይላሉ። (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተውሉ። አጥፊዎች እነርሱ ብቻ ናቸው። ግን እነርሱ ይህን አይገነዘቡም። ሰዎቹ እንዳመኑ እመኑ በተባሉም ጊዜ ቂሎቹ እንዳመኑ እናምናለን? ይላሉ። (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተውሉ። ቂሎቹ እነርሱ ብቻ ናቸው። ግን እነርሱ ይህን አያውቁም።

وَإِذَا لَقُواْ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قَالُوٓاْ ءَامَنَّا وَإِذَا خَلَوْاْ إِلَىٰ شَيَٰطِينِهِمْ قَالُوٓاْ إِنَّا مَعَكُمْ إِنَّمَا نَحْنُ مُسْتَهْزِءُونَ ١٤ ٱللَّهُ يَسْتَهْزِئُ بِهِمْ وَيَمُدُّهُمْ فِي طُغْيَٰنِهِمْ يَعْمَهُونَ ١٥ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱشْتَرَوُاْ ٱلضَّلَٰلَةَ بِٱلْهُدَىٰ فَمَا رَبِحَت تِّجَٰرَتُهُمْ وَمَا كَانُواْ مُهْتَدِينَ ١٦

**14-16.** ከእነዚያ በአላህ በትክክል ካመኑት ሰዎች ጋር በተገናኙ ጊዜ እኛም ልክ እንደናንተው አምነናል ይላሉ። ወደ ሰይጣኖቻቸው ባገለሉ ጊዜ ደግሞ እኛ እኮ ከናንተ ጋር ነን። እኛ (በእነርሱ) ተሳላቂዎች ብቻ ነን ይላሉ። አላህ በእነርሱ ይሳለቅባቸዋል። በአመጻቸውም ውስጥ የሚዋልሉ ሲሆኑ ያቆያቸዋል። እነዚህ እነዚያ ስህተትን በቅንነት የገዙ (የለወጡ) ሰዎች ናቸው። እናም ንግዳቸው ትርፋማ አይደለም። ቅኑን መንገድም አልተከተሉም።

مَثَلُهُمْ كَمَثَلِ ٱلَّذِي ٱسْتَوْقَدَ نَارًا فَلَمَّآ أَضَآءَتْ مَا حَوْلَهُۥ ذَهَبَ ٱللَّهُ بِنُورِهِمْ وَتَرَكَهُمْ فِي ظُلُمَٰتٍ لَّا يُبْصِرُونَ ١٧ صُمٌّۢ بُكْمٌ عُمْيٌ فَهُمْ لَا يَرْجِعُونَ ١٨

**17-18.** የእነርሱ (ንፍቅና) ምሳሌያቸው ልክ እንደዚያ እሳትን እንዳነደደ ሰውና ከዚያ በዙሪያው ያለውን ሁሉ ባበራችለት ጊዜ አላህ ብርሃናቸውን እንደወሰደባቸው እና በጨለማዎች ውስጥ የማያዩ ሆነው እንደተዋቸው (ሰዎች) ብጤ ነው። (እነርሱ መልካሙን ነገር የማይሰሙ) ደንቆሮዎች፤ (የሚጠቅማቸውን ነገር የማይናገሩ) ዲዳዎች፤ (ትክክለኛውን የኢስላምን መንገድ የማያዩ) እውሮች ናቸው። ስለዚህ እነርሱ ከስህተት (መቸውንም) አይመለሱም።

أَوۡ كَصَيِّبٖ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ فِيهِ ظُلُمَٰتٞ وَرَعۡدٞ وَبَرۡقٞ يَجۡعَلُونَ أَصَٰبِعَهُمۡ فِيٓ ءَاذَانِهِم مِّنَ ٱلصَّوَٰعِقِ حَذَرَ ٱلۡمَوۡتِۚ وَٱللَّهُ مُحِيطُۢ بِٱلۡكَٰفِرِينَ ١٩ يَكَادُ ٱلۡبَرۡقُ يَخۡطَفُ أَبۡصَٰرَهُمۡۖ كُلَّمَآ أَضَآءَ لَهُم مَّشَوۡاْ فِيهِ وَإِذَآ أَظۡلَمَ عَلَيۡهِمۡ قَامُواْۚ وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَذَهَبَ بِسَمۡعِهِمۡ وَأَبۡصَٰرِهِمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٢٠

**19-20.** ወይም (ምሳሌያቸው) ከሰማይ እንደወረደ ዝናብ (ባለቤቶች) ነው። በእርሱ (በደመናው) ውስጥ ጨለማዎች፤ ነጎድጓድና ብልጭታ ያሉበት ሲሆን ከመብረቆቹ (ሊመጣ ከሚችል ጥቃት) ሞትን በመፍራት ጣቶቻቸውን በጆሮዎቻቸው ውስጥ እንደሚያደርጉ ሰዎች ቢጤ ነው። አላህ ከሓዲያንን በእውቀቱ ከባቢ ነው። (አይሳኑትም)። ብልጭታው ዓይኖቻቸውን ሊነጥቅ ይቀርባል። ለእነርሱ ባበራላቸው ቁጥር በውስጡ ይሄዳሉ። በእነርሱም ላይ ባጨለመባቸው ጊዜ ደግሞ ይቆማሉ። አላህ በፈለገ ኖሮ መስሚያዎቻቸውንና ማያዎቻቸውን ይወስድባቸው ነበር። አላህ በነገሮች ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (8-20) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከአስመሳዮች ባህሪያት የተወሰኑትን ማውሳት
2. ተግባር የሌለው ንግግር ፋይዳ ቢስ እና ማንም ሰው እንዲህ ነኝ በማለቱ ብቻ ተቀባይነት እንደሌለው፤
3. አስመሳዮች ትክክለኛ አማኞች እንዳልሆኑ እና ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው፤
4. ባስተምህሮት ላይ ነገሮችን ከፋፍሎ ማስረዳት ተገቢ መሆኑን፤
5. አስመሳዮች ተንኮለኞች መሆናቸውን እና ከአስመሳዮች ተንኮል በአቅም ልክ መጠበቅ ግዴታ መሆኑን፤
6. ተንኮል በይበልጥ የሚጎዳው ተንኮለኛን መሆኑን፤
7. መጥፎ ተግባር ህሊናን እንደሚያውር እና አስመሳዮችን ምንም አይነት አስተምህሮት እንደማይጠቅማቸው፤

8. የሰው ልጅ የመጥመሙ ዋና ምክንያት እራሱ እንደሆነ፤
9. ወንጀልም እንደ ኸይር ስራ ሁሉ የመጨመርና የመቀነስ ባህሪ እንዳለው፤
10. ቅጣቶች በምክንያት እንደሚመጡ፤
11. አስመሳዮች የውሸትንና የማስተባበልን ወንጀሎች በአንድ እንዳጠቃለሉ፤
12. ንፍቅና ሀገርን ከሚያበላሹ መጥፎ ተግባራት አንዱ መሆኑን፤
13. ከፈተናዎች ሁሉ መጥፎው የሰው ልጅ ጥፋቱን እንደ ልማት መቁጠሩ መሆኑን፤
14. ትክክለኛ አማኝ ያልሆነ ሰው ምንጊዜም አስተሳሰቡ ጠባብና ሸውራራ መሆኑን፤
15. አስመሳዮች ብዙ ጊዜ ራሳቸውን እንደሚከቡ፤
16. የአላህ ጠላቶች የአላህን ወዳጆች በማይሆን መገለጫ እንደሚገልጿቸው፤
17. ትክክለኛ እምነት የሌለው ሁሉ ሞኝ እንደሆነ፤
18. ከጥበቦች ሁሉ የበለጠው ጥበብ በአላህ እና በህጉ መመራት ብቻ መሆኑን፤
19. አላህ ግፈኞችን ጊዜ ሊሰጣቸው እንደሚችል፤
20. ግፈኞችን የግፍ ተግባራቸው ይበልጥ ለጥፋት እንደሚገፋፋቸው፤
21. ነገርን በምሳሌ ማስረዳት በአዕምሮ ውስጥ ግንዛቤን ለማስረፅ ተመራጭ በመሆኑ በቁርኣን በብዛት የሚታይ መሆኑን፤
22. እምነት ብርሃን እንደሆነ እና አስመሳዮች ግን ምንም ብርሃን እንደሌላቸው፤
23. አስመሳዩች ውሸትን በመፍጠርና በማባዛት ሰዎችን ሊያሳስቱ እንደሚሞክሩ፤
24. ከአስመሳዮች የተወገዘ ባህሪያት መካከል ብልሹ ተግባራትን በምድር ላይ ማስፋፋት አንዱ መሆኑን፤
25. ከሰው ልጆች መካከል ሰይጣናዊ ባህሪ ያላቸው ሰዎችም እንዳሉ
26. አስመሳዮች የአላህ ጥበቃ የተነፈጋቸው እርጉም ፍጡሮች መሆናቸውን፤
27. አስመሳዮች እውነት የሚያዩበት ዓይን፤ ሀቅ የሚናገሩበት ምላስ፤ ሀቅ የሚሰሙበት ጆሮ እንደሌላቸው፤
28. ከሓዲያን ከአላህ ቅጣት የማያመልጡ መሆናቸውን፤
29. ከባድ መብረቅ ዓይን ሊያጠፋ እንደሚችል፤
30. አላህ ፍላጎት እንዳለው፤
31. የሰው ልጅ ዓይኑን ጆሮውን እንዲጠብቅለት አላህን መለመን እንዳለበት፤
32. ውሸትን አንግቦ የሚጓዝ ሁሉ መጨረሻው እስከፊ ውድቀት እንደሆነ፤
33. በምድር ላይ ሲኖሩ መልካም ነገርን በመስራት ምድርን ማሳመር ከዒባዳ ተግባራት አንዱ እንደሆነ እንማራለን።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱعۡبُدُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَتَّقُونَ ٢١
ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ فِرَٰشٗا وَٱلسَّمَآءَ بِنَآءٗ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجَ بِهِۦ مِنَ
ٱلثَّمَرَٰتِ رِزۡقٗا لَّكُمۡۖ فَلَا تَجۡعَلُواْ لِلَّهِ أَندَادٗا وَأَنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ٢٢

**21-22.** እናንተ ሰዎች ሆይ! ያን እናንተንና እነዚያን ከናንተ በፊት የነበሩትን የፈጠረውን ጌታችሁን አላህን በብቸኝነት ተገዙት። (ቅጣትን) ልትጠነቀቁ ዘንድ*። (አላህ) ያ! ለእናንተ ምድርን ምንጣፍ፤ ሰማይን ጣራ ያደረገ ጌታ ነው። ከሰማይ (ዳመና) ውሃን ያወረደና ከዚያ በውሃው ከፍሬዎች ሁሉ ለእናንተ ሲሳይን ያወጣላችሁ ነው። እናም ብቸኛ (ፈጣሪነቱን) የምታውቁ ስትሆኑ ለአላህ በአምልኮ አጋሮችን አታድርጉ።

* «ለዐለ» (ዘንድ) የሚለው ቃል የጥሩን ነገር መሆን ለመከጀል ወይም የመጥፎ ነገርን መከሰት ለመስጋት ወይም ለምክንያት የሚያገለግል ቃል ነው። በቁርአን ዉስጥ ግን እንደሁኔታው መረዳት እንጂ በሁሉም ቦታ በአንድ አይነት መተርጎም ትክክል አይደለም።

وَإِن كُنتُمۡ فِي رَيۡبٖ مِّمَّا نَزَّلۡنَا عَلَىٰ عَبۡدِنَا فَأۡتُواْ بِسُورَةٖ مِّن مِّثۡلِهِۦ وَٱدۡعُواْ شُهَدَآءَكُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٢٣﴾ فَإِن لَّمۡ تَفۡعَلُواْ وَلَن تَفۡعَلُواْ فَٱتَّقُواْ ٱلنَّارَ ٱلَّتِي وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلۡحِجَارَةُۖ أُعِدَّتۡ لِلۡكَٰفِرِينَ ﴿٢٤﴾

**23-24.** (እናንተ ከሃዲያን ሆይ!) በአገልጋያችን (በሙሐመድ) ላይ ባወረድነው ቁርአን በመጠራጠር ላይ ከሆናችሁ ከሱ ጋር ሊወዳደር የሚችል አንድ ምእራፍ እንኳን እስቲ አምጡ። እውነተኞች እንደሆናችሁ ከአላህ ሌላ ረዳቶቻችሁንም ሁሉ ጥሩ። (ይህንን) ባትሰሩ ግን በርግጥም አትሰሩትምና (አትፈጽሙትምና) ያችን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ድንጋዮች ከሆነው ከገሀነም እሳት ራሳችሁን ጠብቁ። ለከሓዲያን ሁሉ ተደግሳለችና።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (21-24) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መሬትን ለሰው ልጆች መኖሪያነት አመቺ አድርጎ የፈጠረው አላህ ሩህሩህ መሆኑን፤
2. ሰማይን ያለ ተሸካሚ ምሰሶ ያቆመውን አላህ ኃያልነት፤
3. ዝናብን ከሰማይ ያወረደውን የአላህ ኃያልነት፤
4. ሁሉም ነገር ምክንያቶች ያሉት ቢሆንም ምክንያቶች ብቻቸዉን በአላህ ፈቃድ እንጂ ምንም ማድረግ እንደማይችል፤
5. ነብዩ (ﷺ) ከአላህ የተላኩ ትክክለኛ ነብይ መሆናቸውን፤
6. የሰው ልጆች ሙሉ ሃይላቸዉን በመጠቀም ቁርኣንን የመሰለ መፅሐፍ ለመፍጠር ቢሞክሩ ሙከራው ከንቱ እንደሚሆን፤
7. ገሀነም ለከሓዲያን የዘላለም ቤት እንዲሆን የተፈጠረና የተዘጋጀ መሆኑን፤
8. አላህ ባሮቹን ሁሉ ከጥቃት እንደሚከላከል፤
9. አላህ ነብዩን (ﷺ) አገልጋዬ ብሎ በመግለፅ በእሱ ዘንድ ያላቸውን ልዩ ከበሬታ መግለፅ፤
10. ቁርኣን በትክክል የአላህ ቃል መሆኑን፤
11. «ያወረድነው» በማለት የአላህን የበላይነት በግልፅ መገንዘብ፤
12. ቁርኣን አጭር ምዕራፍ እንኳን ቢሆን የአላህ ተዐምር መሆኑን፤

13. ቁርኣንን የተቃወመ ሁሉ መጨረሻው እሳት መሆኑን፤
14. ሰዎች የእሳት ማገዶ የሚሆኑበት ቅጣት እንዳለባቸው፤
15. የጀሀነም እሳት አሁንም ተፈጥራና ተዘጋጅታ ያለች መሆኗን፤
16. የገሀነም እሳት የከሓዲያን ሁሉ መቅጫ መሆኗን፤
17. ውሃ በምድር ላለ ሕይወት እንደሚዘራ ሁሉ ቁርኣንም በልብ ውስጥ የእምነት እርካታን የሚዘራ መሆኑን፤
18. ከሓዲያን የተለያዩ የዝቅጠት ደረጃ እንዳላባቸውና በክህደታቸው አይነትና መጠን ተከፋፍለው እንደሚታዩ፤
19. የሰው ችሎታና ተግባር ከአላህ ችሎታ ውጭ ነው የሚሉ ሰዎችን ስህተት ማስረዳት፤
20. የአምልኮት አስፈላጊነትን መጠቆም፤
21. በጌትነቱ ማመንና ብቸኛ አምላክነቱንም እንደሚያስይዝ ማወቅ፤
22. አላህን በብቸኝነት ማምለክ ግዴታ መሆኑን፤
23. አላህን በብቸኝነት ማምለክ አዕምሯችን የሚያስገድደን ጉዳይ መሆኑን፤
24. አላህ ብቸኛ ፈጣሪ መሆኑን የሚያመለክቱ ጉዳዮችን መጥቀሱን፤
25. አላህን መፍራት ተራ ሰው ሊደርስበት የማይችል ከፍተኛ ማዕረግ መሆኑን፤
26. ለሰው ልጅ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን እንማራለን።

وَبَشِّرِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أَنَّ لَهُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۖ كُلَّمَا
رُزِقُواْ مِنۡهَا مِن ثَمَرَةٖ رِّزۡقٗا قَالُواْ هَٰذَا ٱلَّذِي رُزِقۡنَا مِن قَبۡلُۖ وَأُتُواْ بِهِۦ مُتَشَٰبِهٗاۖ وَلَهُمۡ فِيهَآ
أَزۡوَٰجٞ مُّطَهَّرَةٞۖ وَهُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٢٥

**25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑትንና መልካም ተግባራት የሰሩትን ሰዎች ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያሏቸው መሆኑን አብስራቸው። በእርሷም ፍራፍሬ በተለገሱ ቁጥር (ፍሬዎቿ ስለሚመሳሰሉ) ይህማ ያ፣ ከአሁን በፊት የተመገብነው ነው ይላሉ። እርሱ ተመሳሳይ ሆኖ ይሰጣቸዋል (በመልኩ ተመሳሳዩ ቀደም ሲል የቀረበላቸው በመሆኑ ነው። ሆኖም ጠዐሙ የተለያየ ነው)። ለእነርሱም በውስጧ ንፁህ ሚስቶች አሏቸው። እነርሱም በውስጧ ዘወታሪዎች ናቸው።

۞ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَسۡتَحۡيِۦٓ أَن يَضۡرِبَ مَثَلٗا مَّا بَعُوضَةٗ فَمَا فَوۡقَهَاۚ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ فَيَعۡلَمُونَ
أَنَّهُ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّهِمۡۖ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فَيَقُولُونَ مَاذَآ أَرَادَ ٱللَّهُ بِهَٰذَا مَثَلٗاۘ يُضِلُّ بِهِۦ كَثِيرٗا
وَيَهۡدِي بِهِۦ كَثِيرٗاۚ وَمَا يُضِلُّ بِهِۦٓ إِلَّا ٱلۡفَٰسِقِينَ ٢٦ ٱلَّذِينَ يَنقُضُونَ عَهۡدَ ٱللَّهِ مِنۢ بَعۡدِ مِيثَٰقِهِۦ
وَيَقۡطَعُونَ مَآ أَمَرَ ٱللَّهُ بِهِۦٓ أَن يُوصَلَ وَيُفۡسِدُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٢٧

**26-27.** አላህ ማንኛውንም ነገር ትንኝም ትሁን ከሷም በላይ የሆነን ነገር ምሳሌ ከማድረግ አያፍርም። እናም እነዚያ ያመኑ ሰዎች (ምሳሌው) ከጌታቸው (የተነገረ) እውነት መሆኑን ያውቃሉ። እነዚያ የካዱ ሰዎች ግን አላህ በዚህ አባባል ምንን ምሳሌ ፈልጎበት ነው ይላሉ። አላህ በምሳሌው ብዙዎችን ያሳስታል። በእርሱም ብዙዎችን ያቀናል። በእርሱም አመፀኞችን እንጂ ሌላን አያሳስትም። እነዚያ ለአላህ በፅናት የገቡትን ቃል ኪዳን የሚያፈርሱ፤ እንዲቀጠልም በርሱ ያዘዘውን ነገር ሁሉ የሚቆርጡ፤ በምድር ላይ ሁከት የሚፈጥሩ ከሳሪዎች እነርሱ ብቻ ናቸው።

كَيْفَ تَكْفُرُونَ بِٱللَّهِ وَكُنتُمْ أَمْوَٰتًا فَأَحْيَٰكُمْ ۖ ثُمَّ يُمِيتُكُمْ ثُمَّ يُحْيِيكُمْ ثُمَّ إِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿٢٨﴾ هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ لَكُم مَّا فِى ٱلْأَرْضِ جَمِيعًا ثُمَّ ٱسْتَوَىٰٓ إِلَى ٱلسَّمَآءِ فَسَوَّىٰهُنَّ سَبْعَ سَمَٰوَٰتٍ ۚ وَهُوَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ ﴿٢٩﴾

**28-29.** (እናንተ ከሓዲያን ሆይ!) ሙታን የነበራችሁትን ሕያው ያደረጋችሁ፤ ከዚያ የሚገድላችሁ፤ ከዚያ ሕያው የሚያደርጋችሁና ከዚያ ወደ እርሱ የምትመለሱ ስትሆኑ እንዴት በአላህ ትክዳላችሁ! እርሱ (አላህ) ያ፣ በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ ለእናንተ ጥቅም ሲል የፈጠረ ጌታ ነው። ከዚያ ወደ ሰማይ አሰበና ሰባት ሰማያት አደረጋቸው። እርሱ ሁሉን አዋቂ ነውና።

ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (26-29) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አይሁድ በቁርኣን ውስጥ ዝንብ፤ ሸረሪትና የመሳሰሉት ጥቃቅን ነፍሳት መጠቀሳቸውን እያነሱ በቁርኣን ላይ በማፌዛቸው ምክንያት አላህ የፈለገውን ነገር በምሳሌነት መጥቀስ መብቱ መሆኑን ለማሳወቅ የወረዱ የቁርኣን አናቅፅ ናቸው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (25-29) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. እምነት እና ኢስላማዊ መልካም ተግባራት ታላላቅ ትሩፋት ያላቸው ነገሮች መሆናቸውን፤
2. አማኞች ቁርኣን ዉስጥ በተወሱት ምሳሌዎች እንደሚማሩና እንደሚጠቀሙ፤
3. ከሓዲያን ምንም ምሳሌ ቢሰጣቸው እንደማያምኑ፤
4. አላህ ብቸኛ ፈጣሪና የዓለማት ቋሚ አስተናባሪ ለመሆኑ አያሌ ተጨባጭ ማስረጃዎች መኖራቸውን፤
5. ሰዎች በሕይወታቸው ይጠቀሙባቸው ዘንድ ብዙ የምግብ፤ የመጠጥና የአልባሳት አይነት የተፈቀዱ መሆናቸውን፤
6. ቃል ኪዳንን ማፍረስ ከአስመሳዩች ዋና ዋና ምልክቶች አንዱ መሆኑን፤
7. ሰዎችን በሚያስደስት ነገር ማብሰር ተገቢ መሆኑን፤
8. ጀነት በእምነት ብቻ ሳይሆን መልካም ስራንም ለሚተገብሩ ሰዎች መሆኗን፤

9. ጀነት ብዙ ማዕረጎች ያሏት መሆኑን፤
10. በአኼራው ዓለም እንደዚሁ ዓለም ጋብቻ ያለ መሆኑን፤
11. ጀነት የሚገቡ ሰዎች ሁሉ ዘላለም ኗሪዎች መሆናቸውንና ጀነት ለሁልጊዜም የምትኖር የማትጠፋ መሆኗን፤
12. ከሓዲያን የአላህን ህግ መፃረር የተለመደ ባህሪያቸው መሆኑን፤
13. በትክክል በአላህ አማኝ የሆነ ሰው ሁሉ የአላህን ህግ እንደማይፃረር፤
14. አላህ ኃያዕ የሚባል ባህሪ እንዳለው፤
15. በአላህ የሚክዱ ሰዎች ሁሉ ተግባራቸው የሚያስገርም መሆኑን፤
16. ሞት ሩህ ላለው ነገር ሁሉ የማይቀር መሆኑን፤
17. ፅንስ ሩህ ሳይነፋበት እንደነበረው ተገምቶ እንደማይታጠብ፤ እንደማይከፈንና ሶላትም እንደማይሰገድበት እንደማይወርስ፤
18. ከአላህ ኃያልነት መገለጫዎች መካከል፡- ሩህ ያልነበረውን በድን ሩህ በመንፋት አሳቢ፤አስተማሪ፤ ተመራማሪ ሰው ማድረጉ፤
19. የሙቶ መነሳትን እውነትነት በምሳሌ ማረጋገጥ፤
20. ሰዎች ሁሉ መጨረሻቸው እና ሂደው ሂደው መመለሻቸው ወደ አንድ አላህ ብቻ መሆኑን፤
21. መሬትን ለመኖሪያነት አመቺ አድርጎ በመፍጠር አላህ ለሰው ልጆች የዋለውን ውለታ ማስተዋል ተገቢ መሆኑን፤
22. በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ፡- ዛፎች፤ ውሃዎች፤ እንሰሳዎች ከአላህ ወይም ከነብዩ ክልክልነታቸው እስካልመጣ ድረስ የተፈቀዱ መሆናቸዉን፤
23. አላህ ድርጊቶችን እንደአስፈላጊነቱ በፈለገበት አይነትና በሻበት ሰዓት የሚፈፅም መሆኑን፤
24. ሰማያት ሰባት መሆናቸው እና አፈጣጠራቸው ይህ ነደለው የማይባል መሆናቸው።
25. አላህ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ትንሽም ነገር የማይሳተዉ መሆኑን፤
26. አላህን በሁሉ ነገር ልናመሰግነው እንደሚገባ መጠቆም፤
27. አላህን በሁሉ ነገር ልንፈራውና ልናከብረው እንደሚገባን፤
28. አላህ ፍጥረተ ዐለሙን እንዴት እንደተጀመረ እንማራለን።

وَإِذۡ قَالَ رَبُّكَ لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّي جَاعِلٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ خَلِيفَةٗۖ قَالُوٓاْ أَتَجۡعَلُ فِيهَا مَن يُفۡسِدُ فِيهَا
وَيَسۡفِكُ ٱلدِّمَآءَ وَنَحۡنُ نُسَبِّحُ بِحَمۡدِكَ وَنُقَدِّسُ لَكَۖ قَالَ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٣٠ وَعَلَّمَ
ءَادَمَ ٱلۡأَسۡمَآءَ كُلَّهَا ثُمَّ عَرَضَهُمۡ عَلَى ٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ فَقَالَ أَنۢبِـُٔونِي بِأَسۡمَآءِ هَٰٓؤُلَآءِ إِن كُنتُمۡ
صَٰدِقِينَ ٣١ قَالُواْ سُبۡحَٰنَكَ لَا عِلۡمَ لَنَآ إِلَّا مَا عَلَّمۡتَنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡحَكِيمُ ٣٢

**30-32.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላዕክት እኔ በምድር ላይ ወኪል (ምትክን) ላደርግ ነው ባለ ጊዜ (የሆነውን ለህዝቦችህ አስታውስ)። «እኛ ከማመስገን ጋር የምናጠራህ፤ አንተንም የምናሞግስህ ስንሆን በምድር ውስጥ የሚያጠፉንና ደሞችንም የሚያፈስን ፍጡር ታደርጋለህን?» አሉ።

አላህም «እኔ እናንተ የማታውቁትን ነገር ሁሉ አውቃለሁ አላቸው»፡፡ ለአደምም ስሞችን ሁሉ አስተማረው፡፡ ከዚያ በመላዕክት ላይ ተሰያሚዎቹን አቀረባቸው፡፡ እውነተኞች ከሆናችሁ የእነዚህን ተሰያሚዎች መጠሪያ ንገሩኝ አላቸው፡፡ «እነርሱም ጥራት ይገባህ አንተ ካስተማርከን ነገር በስተቀር እኛ ምንም እውቀት የለንም፡፡ አንተ ብቸኛው ጥበበኛና አዋቂ ነህና» አሉ፡፡

قَالَ يَـٰٓـَٔادَمُ أَنۢبِئۡهُم بِأَسۡمَآئِهِمۡۖ فَلَمَّآ أَنۢبَأَهُم بِأَسۡمَآئِهِمۡ قَالَ أَلَمۡ أَقُل لَّكُمۡ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ غَيۡبَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَأَعۡلَمُ مَا تُبۡدُونَ وَمَا كُنتُمۡ تَكۡتُمُونَ ٣٣

**33.** አላህም «አደም ሆይ! ስሞቻቸውን ንገራቸው አለው»፡፡ ከዚያም ስሞቻቸውን በነገራቸው ጊዜ «እኔ የሰማያትንና የምድሩን ሩቅ ምስጢር ሁሉ አውቃለሁ፡፡ የምትገልፁትንና ያንንም ትደብቁት የነበራችሁትን ሁሉ አውቃለሁ አላልኳችሁምን»? አላቸው፡፡

وَإِذۡ قُلۡنَا لِلۡمَلَـٰٓئِكَةِ ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ أَبَىٰ وَٱسۡتَكۡبَرَ وَكَانَ مِنَ ٱلۡكَٰفِرِينَ ٣٤ وَقُلۡنَا يَـٰٓـَٔادَمُ ٱسۡكُنۡ أَنتَ وَزَوۡجُكَ ٱلۡجَنَّةَ وَكُلَا مِنۡهَا رَغَدًا حَيۡثُ شِئۡتُمَا وَلَا تَقۡرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ ٱلظَّـٰلِمِينَ ٣٥ فَأَزَلَّهُمَا ٱلشَّيۡطَٰنُ عَنۡهَا فَأَخۡرَجَهُمَا مِمَّا كَانَا فِيهِۖ وَقُلۡنَا ٱهۡبِطُواْ بَعۡضُكُمۡ لِبَعۡضٍ عَدُوّٞۖ وَلَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُسۡتَقَرّٞ وَمَتَٰعٌ إِلَىٰ حِينٖ ٣٦ فَتَلَقَّىٰٓ ءَادَمُ مِن رَّبِّهِۦ كَلِمَٰتٖ فَتَابَ عَلَيۡهِۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ٣٧

**34-37.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለመላዕክት ለአደም ስገዱ ባልን ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡፡ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር፡፡ ሁሉም ወዲያውኑ ሰገዱ፡፡ እርሱማ እምቢ አለ፡፡ ኮራ ከከሓዲያንም ሆነ፡፡ «አደም ሆይ!አንተና ሚስትህ በገነት ውስጥ ተቀመጡ፡፡ በእርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ እንደልባችሁ በሰፊው ተመገቡ፡፡ ግን ከበደለኞች ትሆናላችሁና ይህችን ዛፍ አትቅረቡ› አልናቸው፡፡ እናም በእርሷ ምክንያት ሰይጣን አሳሳታቸው፡፡ ከዚያ ወዲያውኑ ከነበሩበት ጀነት አወጣቸው፡፡ ከፊላችሁ ለከፊሉ ጠላት ሲሆን ሁላችሁም ከዚህ ውጡ፡፡ ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ጊዜ ሞታችሁ ማረፊያና የአጭር ጊዜ መኖሪያችሁ ይሆናል አልናቸው፡፡ ከዚያ አደም ከጌታው የመታረቂያ ቃል ተማረ፡፡ ጌታውም ተማፅኖውን ተቀበለው፡፡ አላህ ፀፀትን ተቀባይና አዛኝ ነውና፡፡

قُلْنَا ٱهْبِطُوا۟ مِنْهَا جَمِيعًا ۖ فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّى هُدًى فَمَن تَبِعَ هُدَاىَ فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ
يَحْزَنُونَ ﴿٣٨﴾ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَكَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَآ أُو۟لَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٣٩﴾

**38-39.** (አላህም አለ፡- አደምና ሐዋ ሁላችሁም በአንድ ሆናችሁ) ከርሷ (ከገነት) (ወደ ምድር) ውረዱ፡፡ አልናቸው ከዚያ ከእኔ የሆነ መመሪያ ሲመጣላችሁ መመሪያዬን የተከተሉ ሰዎች ሁሉ በእነርሱ ላይ ምንም (ይደርስብናል ብለው) ፍርሀት የለባቸውም፡፡ ምንም (ነገር ያመልጠናል ብለው) አያዝኑምም (አልናቸው)፡፡ እነዚያም (በመልዕክተኞቻችን) የካዱ፤ በራዕያችን ያስተባበሉ ግን እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲሆኑ የእሳት (ገሀነም) ማገዶዎች ናቸው (አልናቸው)፡፡

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (30-39) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ንግግር እንዳለውና መልዕክትንም እንዳናገራቸው፤
2. መላኢኮች አዕምሮ ያላቸው አዋቂዎች መሆናቸውን፤
3. የሰው ልጆች አንዱ ከሌላው የመተካካት ባህሪ ያላቸው ፍጡር መሆናቸውን፤
4. የመላኢኮች ተግባር አላህን ማምለክ መሆኑን፤
5. በምድር ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች መላኢኮች እንደሚከፉ፤
6. ማንም ለኩራት ካልፈለገው እራሱን በጥሩ ነገር መግለፅ መጥፎ እንዳልሆነ፤
7. መላኢኮች ለአላህ ያላቸው አክብሮት ከፍተኛ መሆኑን፤
8. አላህ ፍጡሮችን በእውቀት እንሚያበላልጣቸው እና አንዱ የማያውቀው ሌላው ሊያውቀው እንደሚችል፤
9. ቋንቋዎች በሰዎች ሙከራ የመጡ ሳይሆኑ ከአላህ የተሰጡ እውቀቶች መሆናቸውን፤
10. የአባታችንን አደም ትልቅነት የማሳየትና ከመላኢኮች በላይ መሆናቸውን መግለፅ፤
11. ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል በአላህ ትዕዛዝ ከሆነ ሱጁድ እንኳን ማድረግ እንደሚቻል፤
12. ኩራት ለአላህ ብቻ የተገባ ስለሆነ የሰዎች ባህሪ መሆን እንደሌለበት፤
13. ኢብሊስ የሰውን ልጅ ወደ ጠማማና መጥፎ ጎዳና የሚወስድ የሰው ዘር ሁሉ ግልፅ ጠላት መሆኑን፤
14. ወንጀሎች በአይነትና በመጠን እንደሚለያዩና ወደ ክህደት የሚያመሩ ብሎም በራሳቸው ክህደት የሆኑ እንዳሉ፤
15. የሰው ልጅን በተለያዩ ሙከራዎች ማሳለፉ እንደሚቻል፤
16. የሰዎችን ማንነታቸውን ለማሳወቅ መፈታተን እንደሚቻል፤
17. መላኢኮች ልክ እንደ ሰው እንደሚናገሩ፤
18. መላኢኮች አላህ ያሳወቃቸውን ብቻ እንጂ ሁሉን ነገር እንደማያውቁ በራሳቸው አንደበት ማመናቸውን፤
19. አባታችን አደም ለአላህ ትዕዛዝ በታማኝነት የሚፈፅሙ መሆናቸውን፤
20. የአላህን ሁለንተናዊ አዋቂነት በግልፅ ማስረዳት፤
21. መላኢኮች የሚደበቁና በይፋ የሚታዩ እሳቤዎች እንዳሏቸው፤

22. በማንኛውንም ጉዳይ አላዋቂ አዋቂን በመጠየቅ ትምህርት ሊያገኝ እንደሚገባና መጠየቅ አስፈላጊ የመማሪያ ዘዴ መሆኑን፤
23. በደረሰበት ቁሳዊ ችግር አስገዳጅነት ከሰው ቁሳዊ እርዳታ የሚፈልግን ሰው መሳደብና ማስደንገጥ ተገቢ እንዳልሆነ፤
24. የሰው ልጅ ዝርያ የመጀመሪያ መነሻ አባታችን አደም መሆናቸውን፤
25. አባታችን አደም ከፍ ያለ ማዕረግ ያላቸው የሰው ልጅ ሁሉ አባት መሆናቸውን፤
26. ሙስሊሞች ሁልጊዜ መሪ እንዲኖራቸው ኢስላማዊ ግዴታ መሆኑን
27. አላህ ለሰዎችም የሚስሰማ ንግግር ያለው መሆኑን፤
28. አደምና ሀዋን በጀነት በማስቀመጥ ሰጥቷቸው የነበረውን ክብር፤
29. ጋብቻ ከሰው ልጆች መፈጠር ጋር አብሮ የተጀመረ አላህ የሚወደው ስርአት መሆኑን፤
30. በአባታችን አደም ዘመን ልጁን ማግባት ይፈቀድ እንደነበርና ነብያት በእምነት ነክ አንድ ሁነው በህግጋት እንደሚለያዩ፤
31. የአደም ልጆች በሙሉ ሲፈጠሩ ክብር ያላቸው ሆኖም በወንጀል ውስጥ መዘፈቅ የተሰጠን ክብር እንደሚያስገፍፍ፤
32. ሰይጣን የሰው ልጅን ከጥንት አባቱ ጀምሮ ከአላህ መንገድ ለማሳሳት የቆመ ግልፅ ጠላት መሆኑ፤
33. አላህ ባሪያውን በፈለገው የሚፈትን መሆኑን፤
34. በኢስላማዊ ህግ አንድን ነገር አታድርግ ለማለት አትቅረበው በማለት ማስተማር እንደሚቻል፤
35. ለሁሉ ነገር ምክንያቶች እንዳሉትና አላህ ከፈለገ ያለምንም ምክንያት የሻውን ማድረግ እንደሚችል፤
36. ስህተቶች የሰይጣን ማሳሳቻ ገመዶች መሆናቸውን አውቀን መጠንቀቅ እንዳለብን፤
37. ሰይጣን አያቶቻችን እንዳሞኘ ሁሉ እኛንም ለማሳሳት ስለሚጥር መጠንቀቅ እንዳለብን፤
38. ጀነት ከፍተኛ ቦታ ላይ ያለ መሆኑን፤
39. ሰዎች መኖር የሚችሉት በምድር ላይ እንጂ ከምድር ውጪ ለመኖር የሚደረጉ ሙከራዎች እርባና የሌላቸው መሆኑን፤
40. የሰው ልጆች እድሜያቸው የቱንም ያህል ቢረዝምም የዚህ ዓለም ኑሯቸው ውስን መሆኗን፤
41. አላህ ለአባታችን አደምና ለእናታችን ሐዋ ንሰሃቸውን በመቀበል የዋለላቸውን ውለታ ማስታወስ፤
42. ከአላህ ስሞች ሁለቱን ስሞች በግልፅ ማውሳት፤
43. ከወንጀል ተግባራት በመታቀብ በንሰሀ ወደ አላህ በመመለስ ምህረቱን መጠየቅ ያለውን ከፍተኛ ጥቅም፤
44. አባታችን አደም የነበሩበት ጀነት ከፍተኛ ቦታ ላይ እንደነበር፤
45. አላህ ተናጋሪ መሆኑንና ሰዎች የሚሰሙት መሆኑን፤
46. ሂዳያ ከአላህ ብቻ የሚመጣ መሆኑን፤
47. የጀሀነም እሳት አሁን ተፈጥሮ ያለ መሆኑን፤
48. ክህደት የዘለላም እሳት ውስጥ በመክተት ስቃዩ የበረታ ቅጣት እንደሚያስከትል ማወቅ እንደሚገባ፤
49. ወንጀል የሰው ልጅ ምድራዊ ህይወቱን ጭምር የሚጎዳ እንደሆነ፤
50. ሰዎች በቁርአንና በሐዲስ መመራታቸው ለዱንያም ሆነ ለአኼራ ደስታ ብቸኛና አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን፤
51. ጋኔንም ሆነ የሰው ልጅ ለሁለት እንደሚከፈሉና እነሱም አማኝና ከሃዲ በመባል የሚገለፁ መሆኑን እንማራለን።

يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَتِيَ ٱلَّتِيٓ أَنۡعَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ وَأَوۡفُواْ بِعَهۡدِيٓ أُوفِ بِعَهۡدِكُمۡ وَإِيَّٰيَ
فَٱرۡهَبُونِ ﴿٤٠﴾ وَءَامِنُواْ بِمَآ أَنزَلۡتُ مُصَدِّقٗا لِّمَا مَعَكُمۡ وَلَا تَكُونُوٓاْ أَوَّلَ كَافِرِۭ بِهِۦۖ وَلَا تَشۡتَرُواْ
بِـَٔايَٰتِي ثَمَنٗا قَلِيلٗا وَإِيَّٰيَ فَٱتَّقُونِ ﴿٤١﴾ وَلَا تَلۡبِسُواْ ٱلۡحَقَّ بِٱلۡبَٰطِلِ وَتَكۡتُمُواْ ٱلۡحَقَّ وَأَنتُمۡ
تَعۡلَمُونَ ﴿٤٢﴾ وَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ وَٱرۡكَعُواْ مَعَ ٱلرَّٰكِعِينَ ﴿٤٣﴾ ۞أَتَأۡمُرُونَ ٱلنَّاسَ بِٱلۡبِرِّ
وَتَنسَوۡنَ أَنفُسَكُمۡ وَأَنتُمۡ تَتۡلُونَ ٱلۡكِتَٰبَۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴿٤٤﴾ وَٱسۡتَعِينُواْ بِٱلصَّبۡرِ وَٱلصَّلَوٰةِۚ وَإِنَّهَا
لَكَبِيرَةٌ إِلَّا عَلَى ٱلۡخَٰشِعِينَ ﴿٤٥﴾ ٱلَّذِينَ يَظُنُّونَ أَنَّهُم مُّلَٰقُواْ رَبِّهِمۡ وَأَنَّهُمۡ إِلَيۡهِ رَٰجِعُونَ ﴿٤٦﴾

**40-46.** እናንተ የኢስራኢል ልጆች ሆይ! ያችን በእናንተ ላይ የለገስኳትን ፀጋዬን አስታውሱ። ቃል ኪዳኔን ሙሉ። እኔም ቃልኪዳናችሁን እሞላላችኋለሁና። እኔንም ብቻ ፍሩኝ። (እናንተ የኢስራኢል ልጆች ሆይ!) ከናንተ ጋር ያለውን መፅሐፍ እውቅና የሚሰጥ ሆኖ ባወረድኩት ቁርኣን እመኑ። በእርሱም የመጀመሪያ ከሐዲ አትሁኑ። በራዕይ የተገለፀላችሁን እውነትም ለጥቂት ዋጋ ብላችሁ አትለውጡ። እኔንም ብቻ ፍሩኝ። እውነቱን ከውሸት ጋር አትቀላቅሉ። እናንተም የምታውቁ ስትሆኑ እውነትን አትደብቁ።*1 ሶላትን ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ። ዘካንም ለተገቢው አካል ስጡ። ለጌታችሁም ከአጎንባሾች ጋር አጎንብሱ። (ከሰጋጆች ጋር ስገዱ) እናንተ መፅሐፍን የምታነቡ ሆናችሁና ሰዎችን በበጎ ስራ እያዘዛችሁ ራሳችሁን በመልካም ምግባር ከማነጽ ትዘነጋላችሁን? (ይህ አሳፋሪ ተግባር መሆኑን) አታስተውሉምን?*2 በትግዕስትና በሶላት ጥንካሬንና ብርታትን ለማግኘት እርዳታ ጠይቁ። ሶላት ለእነዚያ ከጌታቸው ጋር እንደሚገናኙና ወደ እርሱ ተመላሾች መሆናቸውን በሚያረጋግጡ ሰዎች ብቻ ላይ እንጂ በሌሎች ላይ ከባድ ነው።

*1 «እውነትን አትደብቁ» የሚለውን በተመለከተ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐጣእ ኢብኑ የሳር እንዳስተላለፉት «ዐብዱላህ ብኑ ዐምር አልዓስን አገኘሁትና «በተውራት ውስጥ ስለተጠቀሱት የአላህ መልዕክተኛ መገለጫዎች ንገረኝ» ብዬ ጠየቅኩት። እሱም «አዎን በአላህ እምላለሁ፤ የአላህ መልዕክተኛ በተውራት ላይ በቁርኣን በገለፃቸው መልካም መገለጫዎች አይነት እንደሚከተለው ተገልፀዋል፡- ነብይ ሆይ! አንተን አማኝ ወደ ሆኑት ሰዎች ምስክር፤ አብሳሪ፤ አስጠንቃቂ፤ ለመሃይማን ቅኑን መንገድ አመላካች አድርገን ልከንሃል። አንተ ባሪያዬም መልዕክተኛዬም ነህ። አልሙተወኪል ብዬም ሰይሜሃለሁ። አንተ አስበርጋጊ ቁጡና በገበያ መካከል ሁከት ፈጣሪ አይደለህም። አንተ መጥፎ ሲሰሩብህ መጥፎ የምትሰራ አይደለህም። ነገር ግን አንተ ግፍ የፈፀሙብህን በመልካም፤ በይቅርታና በርህራሄ የምትቀርብ ነህ። የተጣመመውን መንገድ እስከሚያቀና ድረስና ሰዎች ሁሉ «ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም» እስኪሉ ድረስ በዚህም የአይነ ስውራን አይኖች እስኪበሩ፤ የደንቆሮዎች ጆሮዎች እስኪሰሙና የተዘጉ ልቦች እስኪከፈቱ ድረስ አይገድለውም» ይህ አንቀፅና በዚህ ምዕራፍ ላይ (73. 171. 242. 269) በኣሊ.. ዒምራን ምዕራፍ (7.

190) ላይ በመዐዱ ምዕራፍ (58.103) ላይ እና በሌሎችም ምዕራፎች ላይ ያሉት የቁርኣን አናቅፅ የሚያስተምሩት አዕምሮን በሰፊው መጠቀም አስፈላጊ የመሆኑን እውነታ ነው።

✶2 ይህ ተግባር በይበልጥ በኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ተብራርቷል። የአላህ መልዕክተኛ፡- «አንድ ሰው ወደ ጀሃነም ከመጣ በኋላ ልክ ወፍጮ እንደምታሽከረክር አህያ ጀሀነም ውስጥ ይሽከረከራል። የጀሀነም ሰዎችም በዙሪያው ይሰባሰቡና«አረ እከሌ ሆይ! ሰዎችን በመልካም ታዝዛቸው፤ ከመጥፎም ትከለክላቸው አልነበረምን?» ይሉታል። እሱም «ሰዎችን በመልካም ተግባር አዝዛቸው ነበር። ነገር ግን እኔ ራሴ አልተገብርም ነበር። ከመጥፎም እከለክል ነበር፤ ነገር ግን እኔ ራሴ አልተገብረውም ነበር» ይላል፤ ብለዋል።

የላሟ ምዕራፍ (44)ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ የአይሁድ ምሁራን ራሳቸው ሳያምኑ በኢስላም ያመኑ ዘመዶቻቸውን ግን የያዙት መንገድ ኢስላም እውነት መሆኑን ያረጋግጡላቸውና በእምነታቸውም ላይ እንዲፀኑ ምክር ይሰጧቸው ስለ ነበር ይህ ተግባራቸው እነሱን ከከሐዲነት የማያድናቸው መሆኑን ለመግለፅ የወረደ አንቀፅ ነው። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (40-46) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኢስራኢላዊያንን ወደ እምነት ጥሪ ማድረግ፤
2. ከብዙሀን ህዝብ መካከል የተወሰነውን ክፍል ለይቶ በሆነ ጉዳይ ማናገር የሚቻል መሆኑን፤
3. እውነትን እንዲቀበሉና የአላህን ሀቅ እንዲያከብሩ አላህ የዋለላቸውን ውለታ ማስታወስ ተገቢ መሆኑን፤
4. የአላህን ቃልኪዳን የሞላ ሰው ሁሉ አላህ በቃል ኪዳኑ የሚሞላለት መሆኑን፤ ያፈረሰንም እንደሚቀጣው፤
5. በኢስላም ስለትን መሙላት ግዴታ መሆኑን፤
6. መንፈሳዊ ፍራቻን ለአላህ ብቻ ማድረግ ከአምልኮት ተግባራት አንዱ መሆኑን፤
7. በኒ ኢስራኢሎች ቁርኣንን ተቀብለው ሊያምኑ ግዴታቸው መሆኑን፤
8. ከሃዲ በኢስላም ህግጋት እንደሚገደድ እና ባለመስራቱ እንደሚቀጣበት፤
9. የአላህን ትዕዛዝ በዓለማዊ ጥቅም የቀየረ ሰው ሁሉ የአይሁድ ባህሪ ያለበት መሆኑን፤
10. በዚህ ዓለም ላይ ያሉ ነገሮች ሁሉ የቱንም ያህል ቢበዙ ከአኼራ አንፃር ጥቂት መሆናቸውን፤
11. እውነትን መደበቅ ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
12. በዚህ ዓለም እውነት ወይም ውሸት እንጂ ከሁለቱ ገለልተኛ የሚባል ሌላ ነገር እንደሌለ፤
13. ያለፉት ህዝቦች ሩኩዕ ያላት ሶላት ይሰግዱ እንደነበርና ዘካንም ይሰጡ እንደበር፤
14. ሶላትን በጀመዓ መስገድ በጣም አስፈላጊ መሆኑን፤
15. በእያንዳንዳችን ላይ ያሉትን የአላህን ፀጋዎች እያስታወስን ለእርሱ ምስጋና ማድረስ አስፈላጊ መሆኑን፤
16. አደርገዋለሁ በማለት በቃልም ሆነ በፅሑፍ የገባነውን ቃል ኪዳን መተግበር ግዴታ መሆኑንና ቃል ኪዳን እዳ መሆኑን፤
17. የዕለት ተዕለት የኑሮ እቅስቃሴዎችና ባጠቃላይ የህይወት ጉዞ ላይ እውነትን ብቻ መናገርና መተግበር ግዴታ እንደሆነ፤
18. እውነትና ሀሰትን እየደባለቁ ሰዎችን ማሳሳት ሰዎችን ለጉዳት አሳልፎ እንደመስጠት የሚቆጠር መሆኑን፤
19. ሰዎችን በመልካም ነገር እያዘዙ ራስን ግን ከመልካም ነገሮች ማግለል በኢስላም እጅግ የተወገዘ ፀያፍ ተግባር መሆኑን፤

20. ማንኛውም ሰው ጥፋት ሲሰራ በጥፋቱ ልክ ተጠያቂ ቢሆንም የአዋቂዎች ጥፋት ቅጣት ግን የበለጠ መሆኑን፤
21. የሰው ልጅ ፈታኝ የሆኑ ከባድ ነገሮች ሲያጋጥሙን ትዕግስትን መላበስ ለችግሮቹ መፍትሄ የሚያስገኝ መሆኑን፤
22. በየጊዜው ሞትንና ከዚያም በኋላ የሚያጋጥሙንን ጉዳዩችንና ፈተናዎችን ማስታወሱ አስፈላጊ እንደሆነ፤
23. አላህን ፈሪዎች የሚባሉት እነማንና ምንን ባህሪያት የተላበሱ (ያሟሉ) እንደሆኑ፤
24. ሶላትና ትዕግስት ወደ አላህ የሚያቃርቡ ስለመሆናቸው።
25. መልካም ስራ አላህን ለማይፈሩ ሰዎች ሁሉ በጣም እንደሚከብድ፤
26. አላህ በቂያማ ቀን በግልፅና በማንም በምንም ነገር ያለ መመሰል እንደሚታይ እንማራለን።

يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَتِيَ ٱلَّتِيٓ أَنۡعَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ وَأَنِّي فَضَّلۡتُكُمۡ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٤٧﴾
وَٱتَّقُواْ يَوۡمٗا لَّا تَجۡزِي نَفۡسٌ عَن نَّفۡسٖ شَيۡـٔٗا وَلَا يُقۡبَلُ مِنۡهَا شَفَٰعَةٞ وَلَا يُؤۡخَذُ مِنۡهَا عَدۡلٞ
وَلَا هُمۡ يُنصَرُونَ ﴿٤٨﴾ وَإِذۡ نَجَّيۡنَٰكُم مِّنۡ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ يَسُومُونَكُمۡ سُوٓءَ ٱلۡعَذَابِ يُذَبِّحُونَ
أَبۡنَآءَكُمۡ وَيَسۡتَحۡيُونَ نِسَآءَكُمۡۚ وَفِي ذَٰلِكُم بَلَآءٞ مِّن رَّبِّكُمۡ عَظِيمٞ ﴿٤٩﴾ وَإِذۡ فَرَقۡنَا بِكُمُ
ٱلۡبَحۡرَ فَأَنجَيۡنَٰكُمۡ وَأَغۡرَقۡنَآ ءَالَ فِرۡعَوۡنَ وَأَنتُمۡ تَنظُرُونَ ﴿٥٠﴾ وَإِذۡ وَٰعَدۡنَا مُوسَىٰٓ أَرۡبَعِينَ لَيۡلَةٗ
ثُمَّ ٱتَّخَذۡتُمُ ٱلۡعِجۡلَ مِنۢ بَعۡدِهِۦ وَأَنتُمۡ ظَٰلِمُونَ ﴿٥١﴾ ثُمَّ عَفَوۡنَا عَنكُم مِّنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ لَعَلَّكُمۡ
تَشۡكُرُونَ ﴿٥٢﴾ وَإِذۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَى ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡفُرۡقَانَ لَعَلَّكُمۡ تَهۡتَدُونَ ﴿٥٣﴾ وَإِذۡ قَالَ مُوسَىٰ
لِقَوۡمِهِۦ يَٰقَوۡمِ إِنَّكُمۡ ظَلَمۡتُمۡ أَنفُسَكُم بِٱتِّخَاذِكُمُ ٱلۡعِجۡلَ فَتُوبُوٓاْ إِلَىٰ بَارِئِكُمۡ فَٱقۡتُلُوٓاْ
أَنفُسَكُمۡ ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ عِندَ بَارِئِكُمۡ فَتَابَ عَلَيۡكُمۡۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٥٤﴾

**47-54.** እናንተ የኢስራኢል ልጆች ሆይ! እነዚያን በእናንተ ላይ የለገስኳቸውን አያሌ ፀጋዎችንና (አባቶቻችሁን) በዘመናቸው ከነበሩት የዓለማት ሕዝቦች ሁሉ በላይ ያበለጥኳቸው[*1] መሆኑን (አስታውሱ)። ማንኛዋም ነፍስ ከሌላዋ ነፍስ ምንንም የማትመነዳበትን፤ ከእርሷም ምልጃን የማይቀበሉባትን፤[*2] ከእርሷም ቤዛ የማይያዝባትንና እነርሱም በየትኛውም አካል የማይረዱበትን ቀን ቅጣት ፍሩ (ተጠንቀቁ)። ከፊርዖን ቤተሰቦች (ከሰራዊቱ) ብርቱን ቅጣት የሚያቀምሷችሁ፤ ወንዶች ልጆቻችሁን የሚያርዱና ሴቶች ልጆቻችሁን የሚተዉ ሲሆኑ ከእነርሱ ባዳንናችሁ ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውሱ)። ያ፤ ክስተት ከጌታችሁ ለእናንተ ታላቅ ፈተና ነበር። (እናንተ የኢስራኤል ልጆች ሆይ! በእናንተ ምክንያት ባህሩን በከፈልን ጊዜ የሆነውን ግዙፍ (ታሪክም

አስታውሱ)። ወዲያውኑ አዳንናችሁ። የፈርዖንንም ቤተሰቦች ዓይናችሁ እያየ አሰመጥናቸው)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳ የአርባ ሌሊትን ቀጠሮ ከእኛ በወሰደበት ጊዜ የሆነውን ታሪክ (ለህዝቦችህ አስታውስ)። ከዚያ ከእርሱ መሄድ በኋላ እናንተ ወይፈንን አምላክ አድርጋችሁ ያዛችሁ። ይህን ስትፈፅሙ ስህተት ላይ ነበራችሁ። ቢሆንም ከዚያም ከዚህ በኋላ ታመሰግኑ ዘንድ ለእናንተ ምህረትን አደርግን። እናንተ የኢስራኤል ልጆች ሆይ!ወደ ትክክለኛው መንገድ ትመሩ ዘንድ ለሙሳ እውነትንና ውሸትን የሚለይን መጽሐፍ በሰጠነው ጊዜ (የዋልንላችሁን ውለታ አስታውሱ)። (የኢስራኤል ልጆች ሆይ!) ሙሳ ለሕዝቦቹ፡- ሕዝቦቼ ሆይ!እናንተ ወይፈንን አምላክ አድርጋችሁ በመያዛችሁ ነፍሶቻችሁን በደላችሁ። በመሆኑም ወደ ፈጣሪያችሁ ተመለሱ። ከመካከላችሁ (ወንጀለኛ) ወገኖቻችሁን ግደሉ። ይህ ድርጊት በፈጣሪያችሁ ዘንድ ለእንናተ በላጭ ነው ባለ ጊዜ (የዋልነውን ውለታ አስታውሱ)። በእናንተም ላይ ምህረቱን አወረደ። እነሆ እርሱ ፀፀትን ተቀባይ ምህረተኛ አዛኝ ነውና ባላቸው ጊዜ (የነበረውን ታሪክ አስታውሱ)።

✳1 አባቶቻችሁን በጊዜያቸው ከነበሩት ዓለማት ያበለጥኳቸው ማለት ወይም በዉስጣቸው በነበሩት ነብያት ምክኒያት ከሁሉ ዐለም ያበለጥናችሁ ማለት ነው። ይኸውም በተላከላቸው ነብያት እስካመኑ ድረስ ነው። ይህም ሁኖ ከአለም ህዝብ ሁሉ ምርጥ ናችሁ ከተባሉት ከነብዩ ዑመት ፈፅሞ አይበልጡም።

✳2 በዚህና መሰል አናቅፅ ሊኖር እንደማይችል የተነገረለት ምልጃ ከሓዲያንን በተመለከተ ሲሆን ምእመናንም ቢሆን ያለ አላህ ፍቃድ የሆነውን ማለት ነው እንጂ በአላህ ፈቃድ ለምእመናን የሚደረገው ምልጃ በቁርኣንና በሐዲስ የተረጋገጠ ሐቅ ነው።

وَإِذْ قُلْتُمْ يَٰمُوسَىٰ لَن نُّؤْمِنَ لَكَ حَتَّىٰ نَرَى ٱللَّهَ جَهْرَةً فَأَخَذَتْكُمُ ٱلصَّٰعِقَةُ وَأَنتُمْ
تَنظُرُونَ ﴿٥٥﴾ ثُمَّ بَعَثْنَٰكُم مِّنۢ بَعْدِ مَوْتِكُمْ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴿٥٦﴾ وَظَلَّلْنَا عَلَيْكُمُ
ٱلْغَمَامَ وَأَنزَلْنَا عَلَيْكُمُ ٱلْمَنَّ وَٱلسَّلْوَىٰ ۖ كُلُوا۟ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقْنَٰكُمْ ۚ وَمَا ظَلَمُونَا
وَلَٰكِن كَانُوٓا۟ أَنفُسَهُمْ يَظْلِمُونَ ﴿٥٧﴾

55-57. (የኢስራኤል ልጆች ሆይ!) ሙሳ ሆይ! አላህን በይፋ እስከምናይ ድረስ ለአንተ በፍፁም አናምንልህም ባላችሁ ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውሱ)። እናንተም በዓይናችሁ እየተመለከታችሁ መብረቅ መታችሁ። ከዚያ ታመሰግኑ ዘንድ ከሞታችሁ በኋላ አስነሳናችሁ። (የኢስራኤል ልጆች ሆይ!) ከናንተ ላይ ዳመናን አጠለልን። (እንደ ነጭ ማር ያለ) መንና ድርጭትን ለምግብነት አወረድን። ከሰጠናችሁም ጣፋጮችን ብሉ አልን። እኛን አልበደሉንም። ነፍሶቻቸውን ግን ይበድሉ ነበር።

وَإِذۡ قُلۡنَا ٱدۡخُلُواْ هَٰذِهِ ٱلۡقَرۡيَةَ فَكُلُواْ مِنۡهَا حَيۡثُ شِئۡتُمۡ رَغَدٗا وَٱدۡخُلُواْ ٱلۡبَابَ سُجَّدٗا وَقُولُواْ
حِطَّةٞ نَّغۡفِرۡ لَكُمۡ خَطَٰيَٰكُمۡۚ وَسَنَزِيدُ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٥٨ فَبَدَّلَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ قَوۡلًا غَيۡرَ ٱلَّذِي
قِيلَ لَهُمۡ فَأَنزَلۡنَا عَلَى ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ رِجۡزٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ بِمَا كَانُواْ يَفۡسُقُونَ ٥٩ ۞وَإِذِ ٱسۡتَسۡقَىٰ
مُوسَىٰ لِقَوۡمِهِۦ فَقُلۡنَا ٱضۡرِب بِّعَصَاكَ ٱلۡحَجَرَۖ فَٱنفَجَرَتۡ مِنۡهُ ٱثۡنَتَا عَشۡرَةَ عَيۡنٗاۖ قَدۡ عَلِمَ كُلُّ
أُنَاسٖ مَّشۡرَبَهُمۡۖ كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ مِن رِّزۡقِ ٱللَّهِ وَلَا تَعۡثَوۡاْ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُفۡسِدِينَ ٦٠

**58-60.** (የኢስራኢል ልጆች ሆይ!) ወደዚህች ከተማ ግቡ። ከእርሷም ከፈለጋችሁት ስፍራ ሰፊን (የፈለጋችሁትን ዓይነት ምግብ በፈለጋችሁት መልኩ) ተመገቡ። በሩንም አጎንበሳችሁ ግቡ። ጥያቄያችንም የኃጢአቶታችን መሰረዝ ነው በሉ። ኃጢአቶቻችሁን እንምራለን ለበጎ ሰሪዎችም ምንዳ እንጨምርላቸዋለን ባልን ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውሱ)። እነዚያም እራሳቸውን የበደሉት ሰዎች ከዚያ እነርሱ ከተባሉት ሌላን ቃል ለወጡ። በነዚያም በበደሉት ላይ ያመፁ በመሆናቸው ምክንያት መቅሰፍትን አወረድንባቸው። (የኢስራኤል ልጆች ሆይ!) ሙሳ ለሕዝቦቹ የመጠጥ ውሃን በፈለገ ጊዜ የሆነውን ታሪክ አስታውሱ። ከዚያ ድንጋዩን በዘንግህ ምታው አልነው። መታውም እናም ከእርሱም አስራ ሁለት ምንጮች ፈለቁ (ፈነዱ) ሰዎቹ ሁሉ በትክክል መጠጫቸውን አወቁ። ከአላህ ሲሳይ ብሉ። ጠጡም። አመፀኞችም ሆናችሁ በምድር ላይ አታበላሹ አልናቸው።

وَإِذۡ قُلۡتُمۡ يَٰمُوسَىٰ لَن نَّصۡبِرَ عَلَىٰ طَعَامٖ وَٰحِدٖ فَٱدۡعُ لَنَا رَبَّكَ يُخۡرِجۡ لَنَا مِمَّا تُنۢبِتُ ٱلۡأَرۡضُ
مِنۢ بَقۡلِهَا وَقِثَّآئِهَا وَفُومِهَا وَعَدَسِهَا وَبَصَلِهَاۖ قَالَ أَتَسۡتَبۡدِلُونَ ٱلَّذِي هُوَ أَدۡنَىٰ بِٱلَّذِي هُوَ
خَيۡرٌۚ ٱهۡبِطُواْ مِصۡرٗا فَإِنَّ لَكُم مَّا سَأَلۡتُمۡۗ وَضُرِبَتۡ عَلَيۡهِمُ ٱلذِّلَّةُ وَٱلۡمَسۡكَنَةُ وَبَآءُو بِغَضَبٖ
مِّنَ ٱللَّهِۗ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ كَانُواْ يَكۡفُرُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَيَقۡتُلُونَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّۗ ذَٰلِكَ بِمَا
عَصَواْ وَّكَانُواْ يَعۡتَدُونَ ٦١

**61.** (የኢስራኢል ልጆች ሆይ!) ሙሳ ሆይ! «በአንድ ዓይነት ምግብ ላይ በፍፁም አንታገስም። ስለዚህ ጌታህ ከእነዚያ ምድር ከምታበቅላቸው ከቅጠላ ቅጠሏ፤ ከዱባዋም፤ ከስንዴዋም፤ ከምስሯና ከሽንኩርቷም ያወጣልን ዘንድ ለምንልን» ባላቸው ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውሱ)። ሙሳ ያንን ዝቅተኛ የሆነውን በዚያ ከፍተኛና በላጭ በሆነው ነገር ልትለውጡ ትፈልጋላችሁን?

ወደ ከተማ ውረዱ። ለእናንተም የጠየቃችሁትን ነገር ታገኛላችሁ አላቸው። በውርደትና በድህነት ተንገላቱ። የአላህ ቁጣ ሰፈነባቸው። ይህ እነርሱ በአላህ ተዐምራት መጽሐፍ ይክዱና ነብያትንም ያለ አግባብ ይገድሉ ስለነበሩ ኃጢአት ላይ በመዘፈቃቸውና እንዲሁም ወሰን የሚያልፉ በመሆናቸው ነው።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (47-61) ከምንገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በኒ ኢስራኢሎች የአላህን ፀጋ ማስታወስ ግዴታቸው እንደሆነ፤
2. በኒ ኢስራኤሎች በጊዜው ከነበሩ ሰዎች የተሻሉ እንደነበሩ፤
3. ሰዎች በደረጃ እርስ በራሳቸው እንደሚበላለጡ፤
4. የቂያማ ቀን ጉዳይ የሰው ልጆች በደንብ ሊያስቡበት እንደሚገባ፤
5. የቂያማ ዕለት አንድ ህይወት ለሌላ ህይወት እንደዚህኛው ዓለም ሁሉ እንደማይጠቅም፤
6. የቂያማ ዕለት ችግር በጉቦ፤ በመደለያ፤ በማታለያ፤ የማይታለፍ እውነት ብቻ የሚሰፍንበት ቀን መሆኑን፤
7. የቀብር ቅጣት ከባድ ስለመሆኑና የሽርክ ተግባራት ደግሞ ለዚህ አይነቱ ቅጣት ከሚዳርጉት ወንጀሎች መካከል መሆኑን፤
8. ከሺርክና ከወንጀል ተግባራት ከቀብርና ከቂያማ ቀን ቅጣት መጠበቅ ግዴታ መሆኑን፤
9. የከሃዲ ሽምግልና ተቀባይነት እንደማይሰጠው፤
10. በትንሳኤ ዕለት እከሌ ፊዳ ይሆንልኛል የሚል እምነት መያዙ ተቀባይነት እንደሌለው እንማራለን።
11. የአላህን ፀጋዎች ማስታወስ እርሱን ለማመስገን እንደሚገፋፋና እንደሚያነሳሳ፤
12. አላህ ፈተናዎችን በሚወዳቸው ባሪያዎቹ ላይ እንደሚያበዛ በመገንዘብ ፈተናዎች የገጠሙት ሁሉ ማማረር እንደማይገባው፤
13. ሽርክ ለአላህ ብቻ መሆን የሚገባውን የዒባዳን ዘርፍ ለማይገባው አካል ማድረግ ሲሆን ይህም ከፍተኛ በደል እንደሆነ፤
14. የነብያት መላካቸውና የመፅሐፍት መውረዳቸው ሰዎችን ከተሳሳተ መንገድ ወደ ቀናው ጎዳና ለመምራት መሆኑን፤
15. ውሃ፤ እሳት፤ ክፉ እንሰሳና ሌሎችም ጎጂ ነገሮች ሁሉ በአላህ ፈቃድ ሰውን መጉዳት የማይችሉበት አጋጣሚ እንዳለ፤
16. አላህ የባሪያውን ጥፋት እያየው ማጥፋቱና እራሱን ነፃ ማድረጉ በያዘው ዓላማ ላይ እንዲቀጥል ማድረጉ ሞራል እንደሚሰጥ፤
17. በአንድ ጊዜ ተውራትን ማውረድ እየቻለ ለሰላሳ ቀን ከዚያም አስር ቀን በመጨመር አርባ ቀን እንዲጠብቁ ማድረጉ ሰዎች ለሁሉም ነገር መቸኮል እንደሌለባቸው ለማስተማር እንደሆነ፤
18. ለተወሰኑ ቀናት አስተማሪ ባለመኖሩ ጣኦት በማምለካቸው መቅሰፍት ሳያወርድባቸው መቅረቱ የአላህን ቻይነት ማሳየቱ፤
19. ለሰው ልጆች መመሪያ የሚሆን አስተማሪ የሆነ መፅሐፍ ማግኘታቸው ከአላህ ፀጋዎች አንዱ መሆኑን፤
20. ነብዩ ሙሳ ከታላቅ ነብያት አንዱ መሆናቸውን፤
21. ትክክለኛው ተውራት ከታላላቅ መፅሐፍት ውስጥ አንዱ መሆኑ፤

22. ቀና መንገድን የሚፈልግ ሁሉ ከሰማይ ከወረዱ ቅዱሳን መፅሐፍት እንጂ ከምንም የሚገኝ አለመሆኑን ማወቅ እንዳለበት፤
23. የመኖር ዋናው ትርጉሙና ጥቅሙ አላህን እያመሰገኑ መኖር መሆኑን፤
24. በሕይወታችን እንድናከናውናቸው የተፈቀዱም ሆኑ እንድንርቃቸው የተከለከልናቸው ከአላህና ከነቢዩ ብቻ መሆናቸውን፤
25. ኸይር ስራዎች እንደሚበላለጡ፤
26. ወንጀለኞች የቱንም ያህል ወንጀላቸው ቢከብድ ወደ አላህ ንሰሃ ከገቡ እንደሚቀበላቸው፤
27. የሰው ልጆች አንደ አንድ ህይወት መሆናቸው የበኒ እስራኢሎች ሞኝነት፤
28. ከአቅሙ በላይ የሆነን ነገር የጠየቀ ሰው መቀጣት እንደሚገባው፤
29. አላህ ሰዎችን ገሎ የማዳን ብቃት ያለው መሆኑ፤
30. ዳመና የሚንቀሳቀሰው በአላህ ፈቃድ መሆኑን፤
31. በኒ ኢስራኢሎችን ያለምንም ልፋትና ውጣ ውረድ ምርጥ ምግብ አምጥቶ በማብላት ፀጋውን ማሳየቱን፤
32. ሀላል ነገር መመገብ የሚፈቀድ ሲሆን ሀራም ነገር መመገብ ክልክል መሆኑን፤
33. ወንጀለኞች በወንጀላቸው እራሳቸውን እንጂ ማንንም እንደማይጎዱ፤
34. የእስራኢል ልጆች በወይፈን ቅርፅ የሰሩትን ጣኦት ተገዝተው አፀያፊ ሽርክ ውስጥ ከገቡ በኋላ እንዴት እንደተመለሱ፤
35. ከኢስላም አፈንግጦ የወጣ የሚሰጠው ሸሪዓዊ ብያኔ የሞት ቅጣት መሆኑን፤
36. ዝናብን ለማግኘት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መለመን ተገቢ መሆኑን፤
37. አላህ የፍጡሮቹ የሁልጊዜ ብቸኛው መጠጊያ መሆኑን፤
38. ነብያትም እንደሌላው ሰው ሁሉ ወደ አላህ ችግራቸውን እንደሚያቀርቡ፤
39. ነብያት የፈለጉትን እንደፈለጉ ማድረግ እንደማይችሉ፤
40. ነብዩ ሙሳ ለህዝቦቻቸው አዛኝ እንደነበሩ፤
41. አላህ ቻይ፤ ቸርና ሰሚ እንደሆነ፤
42. አላህ ሁሉን ነገር ሁን ካለው መሆን የሚችል መሆኑንና፤ በዘንግ ተመትቶ ውሃ ሲፈልቅ ማሳየቱን፤
43. የምንጩን ክፍል አስራ ሁለት ቦታ በማድረግ በኒ. ኢስራኢሎች እርስ በራሳቸው እንዳይጋፉ የማስቻሉን ጥበብ፤
44. አላህ በምድር ላይ የፈጠረው ምግብ፤ መጠጥ ሁሉ የሚከለክል ህግ እስካልወረደበት ድረስ ሁሉም ሀላል መሆኑን፤
45. በመሬት ላይ ክፋትን መፈፀም ከባድ ወንጀል መሆኑን፤
46. ያን ወደር የለሽ ምግብ ቀይርልን በማለት ነብዩ ሙሳን ያዋከቡ የነበሩትን በኒ ኢስራኢሎች ባህሪ አስቀያሚነት፤
47. ጌታችንን ሳይሉ ጌታህን በማለት ምን ያህል ትዕቢተኞች እንደነበሩ፤
48. በየትኛውም ጊዜ ቢሆን የተሻለን ነገር ትቶ ወደ አነስተኛ የሚያዘነብል ሰው ወደ አይሁድ ባህሪ የሚዘነበል መሆኑን፤
49. ማንም በምግብም ሆነ በመጠጥ ወደ ኢስራፍ እስካልደረሰ ድረስ እንደማይነወር፤
50. ባቄላ፤ ዱባ፤ ምስር፤ ሽንኩርት ለሰዎች የተፈቀዱ መሆናቸውን እንማራለን።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَٱلَّذِينَ هَادُوا۟ وَٱلنَّصَٰرَىٰ وَٱلصَّٰبِـِٔينَ مَنْ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ
وَعَمِلَ صَٰلِحًا فَلَهُمْ أَجْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ٦٢

**62.** እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑ፤ እነዚያም አይሁዳውያን፤ ክርስቲያኖችና ምንም እምነት የሌላቸው ሳቢያኖች ሁሉ ከነርሱ መካከል በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመኑና መልካምን ስራ የሰሩ ሰዎች ሁሉ በእነርሱ ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም፡፡ ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው አያዝኑምም፡፡

وَإِذْ أَخَذْنَا مِيثَٰقَكُمْ وَرَفَعْنَا فَوْقَكُمُ ٱلطُّورَ خُذُوا۟ مَآ ءَاتَيْنَٰكُم بِقُوَّةٍ وَٱذْكُرُوا۟ مَا فِيهِ
لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ٦٣ ثُمَّ تَوَلَّيْتُم مِّنۢ بَعْدِ ذَٰلِكَ ۖ فَلَوْلَا فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُۥ لَكُنتُم
مِّنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ٦٤ وَلَقَدْ عَلِمْتُمُ ٱلَّذِينَ ٱعْتَدَوْا۟ مِنكُمْ فِى ٱلسَّبْتِ فَقُلْنَا لَهُمْ كُونُوا۟ قِرَدَةً
خَٰسِـِٔينَ ٦٥ فَجَعَلْنَٰهَا نَكَٰلًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهَا وَمَا خَلْفَهَا وَمَوْعِظَةً لِّلْمُتَّقِينَ ٦٦

**63-66.** (የኢስራኢል ልጆች ሆይ!) ከበላያችሁ የጡርን ተራራ ያነሳን ሆነን ከእሳት ቅጣት ትጠበቁ ዘንድ የሰጠናችሁን በርትታችሁ ያዙ፡፡ በውስጡ ያለውን ነገር አስታውሱ ብለን የጠበቀ ቃል ኪዳናችሁን በያዝንበት ጊዜ የሆነውን ታሪክ (ልብ በሉ)፡፡ ከዚያም ከዚህ በኋላ ቃልኪዳኑን ተዋችሁ፡፡ በእናንተ ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ በትክክል ከጠፊዎች ሕዝቦች በሆናችሁ ነበር፡፡ እነዚያንም ከናንተ መካከልም በቅዳሜ ቀን (አሳን በማጥመድ) ወሰን ያለፉትንና ለእነርሱ ወራዳዎች ስትሆኑ ዝንጀሮዎች ሁኑ ያልናቸውን ሕዝቦች ታሪክ በእርግጥ ታውቃላችሁ፡፡ እነዚያን የመንደሯን ሰዎች ቅጣትም ለእነዚያ በጊዜያቸው ለነበሩትና ለእነዚያም ከበኋላቸው ለሚመጡት ሕዝቦች መቀጣጫ (ለፈራሂያንም ትምህርት) አደረግናት፡፡

وَإِذْ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوْمِهِۦٓ إِنَّ ٱللَّهَ يَأْمُرُكُمْ أَن تَذْبَحُوا۟ بَقَرَةً ۖ قَالُوٓا۟ أَتَتَّخِذُنَا هُزُوًا ۖ قَالَ أَعُوذُ
بِٱللَّهِ أَنْ أَكُونَ مِنَ ٱلْجَٰهِلِينَ ٦٧ قَالُوا۟ ٱدْعُ لَنَا رَبَّكَ يُبَيِّن لَّنَا مَا هِىَ ۚ قَالَ إِنَّهُۥ يَقُولُ
إِنَّهَا بَقَرَةٌ لَّا فَارِضٌ وَلَا بِكْرٌ عَوَانٌۢ بَيْنَ ذَٰلِكَ ۖ فَٱفْعَلُوا۟ مَا تُؤْمَرُونَ ٦٨ قَالُوا۟ ٱدْعُ لَنَا
رَبَّكَ يُبَيِّن لَّنَا مَا لَوْنُهَا ۚ قَالَ إِنَّهُۥ يَقُولُ إِنَّهَا بَقَرَةٌ صَفْرَآءُ فَاقِعٌ لَّوْنُهَا تَسُرُّ ٱلنَّٰظِرِينَ ٦٩
قَالُوا۟ ٱدْعُ لَنَا رَبَّكَ يُبَيِّن لَّنَا مَا هِىَ إِنَّ ٱلْبَقَرَ تَشَٰبَهَ عَلَيْنَا وَإِنَّآ إِن شَآءَ ٱللَّهُ لَمُهْتَدُونَ ٧٠
قَالَ إِنَّهُۥ يَقُولُ إِنَّهَا بَقَرَةٌ لَّا ذَلُولٌ تُثِيرُ ٱلْأَرْضَ وَلَا تَسْقِى ٱلْحَرْثَ مُسَلَّمَةٌ لَّا شِيَةَ فِيهَا ۚ
قَالُوا۟ ٱلْـَٰٔنَ جِئْتَ بِٱلْحَقِّ ۚ فَذَبَحُوهَا وَمَا كَادُوا۟ يَفْعَلُونَ ٧١

**67-71.** ሙሳ ለህዝቦቹ «አላህ አንዲትን ላም እንድታርዱ ያዛችኋል» ባለ ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውሱ)። (እነርሱም «ለሙሳ) መሳለቂያ አድርገህ ትይዘናለህን?» አሉት። እሱም«ከተሳላቂዎች ከመሆን በአላህ እጠበቃለሁ» አላቸው። (እነርሱም) «እስቲ ጌታህን ጠይቅልን። እርሷ ምን እንደሆነች (እድሜዋን) ያብራራልን» ዘንድ አሉ። እርሱም እርሷ በውልም ያላረጀችና ጥጃም ያልሆነች በዚህ መካከል ልከኛ የሆነች ጊደር ናት ይላችኋል። የታዘዛችሁትንም ስሩ አላቸው። (እነርሱም) "እስቲ ጌታህን እንደገና ጠይቅልን። መልኳ ምን እንደሚመስል ይገልፅልን ዘንድ» አሉ። እርሱም ‹መልኳ ደማቅ ተመልካቾችን የምታስደስት ዳልቻ ላም ናት ይላችኋል» አላቸው። «ለኛ ጌታህን ጠይቅልን። እርሷ ምን እንደሆነች ይግለፅልን። ምክንያቱም ላሞቹ በሙሉ በእኛ ላይ ተመሳሰሉብን። እኛም አላህ የሻ እንደሆነ በእርግጥ ትክክለኛውን አቅጣጫ የምንይዝ ተመሪዎች ነን» አሉ። እርሱም እርሷ ያልተገራች ምድርን በማረስ የማታስነሳ፤ እርሻንም የማታጠጣ፤ ከነውር ሁሉ ነፃ የሆነች፤ ልዩ ምልክት የሌለባት ናት ይላችኋል አላቸው። (‹እነርሱም) አሁን ገና በትክክል መጣህ› አሉ። ከዚያ ትዕዛዙን ለመፈፀም ቅርብ ያልነበሩ ቢሆኑም በግዳቸው ላሟን ከየትም አፈላልገው በመግዛት አረዷት።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (62-71) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በእምነት ዙሪያ ለመዳን ያለፈ ታሪክና የገዘፈ ስም እንደማያዋጣና የሚጠቅመው ተግባርን ማሳመር ብቻ መሆኑን፤
2. ትክክለኛውን መንገድ የያዙ ሰዎች በፅድቅነት እንደተበሰሩ፤
3. የአላህ ፀጋ የተትረፈረፈላቸው ሁሉ በአግባቡ መጠቀም እና ለሰጣቸው ፀጋ ጥልቅ ምስጋና ማቅረብ እንደሚገባቸው፤
4. ህገ ወጥና መጥፎ ባህሪያት የሚንፀባረቅባቸውን ሰዎች መገሰፅና ማስጠንቀቅ፤
5. ወንጀሎች ባጠቃላይ የተወገዙ ቢሆኑም በተለይ ነብያትና የነርሱን ፈለግ በመከተል ህዝቡን የኢስላምን መሰረት የሚያስጨብጡን ማወክ እጅግ የከፋ ወንጀል መሆኑንና ከአላህ በኩል የሚሰጠው ቅጣትም የከፋ እንደሆነ፤
6. የአላህን ህግጋት ማክበርና ለተፈፃሚነቱም መተባበር ግዴታ ከሆኑ የኢስላም ድንጋጌዎች ውስጥ እንደሚካተት፤
7. አላህን የሚፈራ ማለት የእርሱን ትዕዛዛት በትክክል የሚተገብር ሰው ማለት እንደሆነ፤
8. የተለያዩ ዘዴዎችን እንደ ሽፋን በመጠቀም የአላህን ህግ መጣስ ከወንጀል ነፃ እንደማያደርግ፤
9. በነብዩ ሙሳ ዘመን የነበሩ ሰዎች እጅግ አስቸጋሪ መጥፎ ባህሪያት እንደነበራቸውና እነዚህም ባህሪያት ማውገዝ፤
10. የአላህ ህግጋት ምሉዕና ስህተት የሌለባቸው በመሆናቸው በሙሉም ሆነ በከፊል ከመቃወም መጠንቀቅ እንደሚገባን፤

11. በአላህ የታዘዙ ተግባራት ሁሉ ተመጥነው የተዘጋጁ በመሆኑ እንደወረዱ መተግበር እንጂ ቀላልና ገር የሆኑ ትዕዛዞችን ብቻ በመፈፀም ከባድ ተግባራት እራስን ማግለሉ አስፈላጊ እንዳልሆነ፣
12. በማንኛውም እንቅስቃሴ ላይ የአላህ እገዛ ወሳኝ በመሆኑ በመጀመሪያ ላይ አላህ ካለ እፈፅማለሁ ማለት እስፈላጊ መሆኑን፣
13. የነብያትን ፈለግ በተከተሉ መምህራንን ሞራል የሚነኩ ትችቶችና ተግባራዊ እርምጃዎች እጅግ የተወገዙና በዳዕዋው ላይ የተሰነዘሩ ተደርገው ስለሚታሰቡ ከእነዚህ አይነት ድርጊቶች መቆጠብ ያለውን አስፈላጊነት እንማራለን።

وَإِذۡ قَتَلۡتُمۡ نَفۡسٗا فَٱدَّٰرَٰٔتُمۡ فِيهَاۖ وَٱللَّهُ مُخۡرِجٞ مَّا كُنتُمۡ تَكۡتُمُونَ ﴿٧٢﴾ فَقُلۡنَا ٱضۡرِبُوهُ
بِبَعۡضِهَاۚ كَذَٰلِكَ يُحۡيِ ٱللَّهُ ٱلۡمَوۡتَىٰ وَيُرِيكُمۡ ءَايَٰتِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ﴿٧٣﴾ ثُمَّ قَسَتۡ
قُلُوبُكُم مِّنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ فَهِيَ كَٱلۡحِجَارَةِ أَوۡ أَشَدُّ قَسۡوَةٗۚ وَإِنَّ مِنَ ٱلۡحِجَارَةِ لَمَا يَتَفَجَّرُ مِنۡهُ
ٱلۡأَنۡهَٰرُۚ وَإِنَّ مِنۡهَا لَمَا يَشَّقَّقُ فَيَخۡرُجُ مِنۡهُ ٱلۡمَآءُۚ وَإِنَّ مِنۡهَا لَمَا يَهۡبِطُ مِنۡ خَشۡيَةِ ٱللَّهِۗ وَمَا
ٱللَّهُ بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعۡمَلُونَ ﴿٧٤﴾

**72-74.** (የኢስራኢል ልጆች ሆይ!) ነፍስንም በገደላችሁና በእርሷም ጉዳይ በተከራከራችሁ ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውሱ)። አላህ ያን በውስጣችሁ ትደብቁት የነበራችሁትን ሚስጢር ሁሉ ገላጭ ነው። የሙቱን (በድን) (በታረደችው) በላሚቱ ከፊል አካል ምቱት አልን። (እናም መቱትና ተነሳ)። (የገደለው ማን እንደሆነ ነገራቸውና እንደገና ሞተ)። (ሰዎች ሆይ!) ልክ እንደዚሁ ትገነዘቡና ታውቁ ዘንድ ሙታንን ህያው በማድረግ ተዓምራቶችን ያሳያችኋል። ከዚያም ልቦቻቸው ከዚህ (ትዕይንት) በኋላ ደረቁ። እርሷም በድርቅና እንደ አለት ድንጋዩች ወይም ከእርሱ ይበልጥ የበረቱ ናቸው። ምክንያቱም ከድንጋዩች መካከል ጅረቶች (ወንዞች) የሚፈሱበት፣ ከእነርሱም የሚሰነጥቅና ከእርሱ ውሃ ምንጭ የሚወጣው፣ ከእነርሱም አላህን ከመፍራቱ የተነሳ ወደ ታች የሚወርድ አልለና*። አላህ ከምትሰሩት ነገር ሁሉ (አንዱንም) ዘንጊ አይደለም።

* ድንጋይ፣ ባህር፣ ጋራ፣ ዛፍ፣ ንፋስ፣ ሰማይ፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት እና መሰል ግዑዝ ነገሮች የማሰብና የመረዳት አቅም አላቸው ወይንስ እንዴት ነው ለሚለው የተፍሲር ምሁራን አላህ የመረዳት አቅም ሊሰጣቸው ይችላል ይላሉ። እነዚህ ነገሮች በቁርአን በሐዲስ አላህን እንደሚያጠሩት እንደሚገዙት በብቸኛ አምላክነቱ እንደሚመሰክሩ እነደሚናፍቁ እንደሚወዱ እንደሚጠሉ ተወስቷልና።

۞ أَفَتَطۡمَعُونَ أَن يُؤۡمِنُواْ لَكُمۡ وَقَدۡ كَانَ فَرِيقٞ مِّنۡهُمۡ يَسۡمَعُونَ كَلَٰمَ ٱللَّهِ ثُمَّ يُحَرِّفُونَهُۥ مِنۢ
بَعۡدِ مَا عَقَلُوهُ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ٧٥ وَإِذَا لَقُواْ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قَالُوٓاْ ءَامَنَّا وَإِذَا خَلَا بَعۡضُهُمۡ
إِلَىٰ بَعۡضٖ قَالُوٓاْ أَتُحَدِّثُونَهُم بِمَا فَتَحَ ٱللَّهُ عَلَيۡكُمۡ لِيُحَآجُّوكُم بِهِۦ عِندَ رَبِّكُمۡۚ أَفَلَا
تَعۡقِلُونَ ٧٦ أَوَلَا يَعۡلَمُونَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا يُسِرُّونَ وَمَا يُعۡلِنُونَ ٧٧ وَمِنۡهُمۡ أُمِّيُّونَ
لَا يَعۡلَمُونَ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّآ أَمَانِيَّ وَإِنۡ هُمۡ إِلَّا يَظُنُّونَ ٧٨ فَوَيۡلٞ لِّلَّذِينَ يَكۡتُبُونَ ٱلۡكِتَٰبَ
بِأَيۡدِيهِمۡ ثُمَّ يَقُولُونَ هَٰذَا مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ لِيَشۡتَرُواْ بِهِۦ ثَمَنٗا قَلِيلٗاۖ فَوَيۡلٞ لَّهُم مِّمَّا كَتَبَتۡ
أَيۡدِيهِمۡ وَوَيۡلٞ لَّهُم مِّمَّا يَكۡسِبُونَ ٧٩

**75-79.** ከአይሁዶች መካከል የአላህን ቃል የሚሰሙና ከዚያ እውነቱን ከተረዱ በኋላ ሆን ብለው እነሱ እያወቁ የሚለውጡት ቡድኖች ያሉ ሲሆን ለእናንተ ማመናቸውን ትከጅላላችሁን? እነዚያንም በአላህ ያመኑትን ሙስሊሞችን ባገኙ ጊዜ «እኛም እንደናንተው አምነናል ይላሉ። እርስ በርሳቸው ብቻ በተገናኙ ጊዜ ግን «አላህ በእናንተ ላይ የገለፀላችሁን ነገር በጌታችሁ ዘንድ እርሱን መረጃ እንዲያቀርቡባችሁ ትነግሯቸዋላችሁን? አታስተውሉምን? ይባባላሉ። አላህ የሚደብቁትንም ሆነ የሚገልፁትን ነገር ሁሉ የሚያውቅ ጌታ መሆኑን አያውቁምን? ከእነርሱም መካከል መጽሐፍን (ኦሪትንና ወንጌልን) የማያውቁ መሃይማን አሉ። ግን ከንቱ ምኞቶችን ይመኛሉ። እነርሱም የሚጠራጠሩ እንጂ ትክክለኛ እውቀት የላቸውም። እነዚያ መጽሐፍን በእጆቻቸው ለሚፅፉና ከዚያ በእርሱ ጥቂት ዋጋ ሊገዙበት ብለው ይህ ከአላህ ዘንድ የወረደ ነው ለሚሉ ሰዎች ሁሉ ወዮላቸው። እነርሱ ከዚያ እጆቻቸው ከፃፉት ወንጀል ወዮላቸው። እነርሱ ከዚያ ከሚሰሩት ኃጢአት ወዮላቸው።

وَقَالُواْ لَن تَمَسَّنَا ٱلنَّارُ إِلَّآ أَيَّامٗا مَّعۡدُودَةٗۚ قُلۡ أَتَّخَذۡتُمۡ عِندَ ٱللَّهِ عَهۡدٗا فَلَن يُخۡلِفَ
ٱللَّهُ عَهۡدَهُۥٓۖ أَمۡ تَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٨٠ بَلَىٰۚ مَن كَسَبَ سَيِّئَةٗ وَأَحَٰطَتۡ
بِهِۦ خَطِيٓـَٔتُهُۥ فَأُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٨١ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ
ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٨٢

**80-82.** አይሁድ «የገሀነም እሳት ለተቆጠሩ ውስን ቀናት ብቻ እንጂ ፈፅሞ አትነካንም አሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) «በዚህ ጉዳይ ከአላህ ዘንድ ቃል ኪዳን ይዛችኋልን? ይህ ከሆነ አላህም ኪዳኑን አያፈርስም። ወይስ

በአላህ ላይ የማታውቁትን ትናገራላችሁ በላቸው። እንዴታ (ትነካቸዋለች) መጥፎን ተግባር የሰሩና በኃጢአትም የተከበቡ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱም በውስጧ ለዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው። እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑ እና በጎ ስራዎችን የሰሩ ሁሉ የገነት ጓዶች ናቸው። እነርሱም በውስጧ ለዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው።

ከላሟ ምዕራፍ. ከ (77-82) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የአይሁዶች የጡት ወንድሞች ጎረቤቶች ከመሆናቸውም በተጨማሪ የቅርብ ወዳጆች በነበሩት እና አይሁዶች እንዲሰልሙ ከፍተኛ ምኞት በነበራቸው አንሷሮች እና አይሁድ የዚህ ዓለም እድሜ ሰባት ሺህ ዓመት ብቻ ሲሆን በጥፋታችን የምንቀጣው ለአንድ ሺ አመት በአኼራ የአንድ ቀን ሂሳብ ነው በማለት ለሚያወሩትና በዝሙት ጉዳይ ላይ ለቀያየሩት የሐሰት ወሬ የተሰጠ ምላሽ ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَإِذۡ أَخَذۡنَا مِيثَٰقَ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ لَا تَعۡبُدُونَ إِلَّا ٱللَّهَ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَانٗا وَذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ
وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَقُولُواْ لِلنَّاسِ حُسۡنٗا وَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ ثُمَّ تَوَلَّيۡتُمۡ
إِلَّا قَلِيلٗا مِّنكُمۡ وَأَنتُم مُّعۡرِضُونَ ٨٣ وَإِذۡ أَخَذۡنَا مِيثَٰقَكُمۡ لَا تَسۡفِكُونَ دِمَآءَكُمۡ وَلَا
تُخۡرِجُونَ أَنفُسَكُم مِّن دِيَٰرِكُمۡ ثُمَّ أَقۡرَرۡتُمۡ وَأَنتُمۡ تَشۡهَدُونَ ٨٤ ثُمَّ أَنتُمۡ هَٰٓؤُلَآءِ تَقۡتُلُونَ
أَنفُسَكُمۡ وَتُخۡرِجُونَ فَرِيقٗا مِّنكُم مِّن دِيَٰرِهِمۡ تَظَٰهَرُونَ عَلَيۡهِم بِٱلۡإِثۡمِ وَٱلۡعُدۡوَٰنِ
وَإِن يَأۡتُوكُمۡ أُسَٰرَىٰ تُفَٰدُوهُمۡ وَهُوَ مُحَرَّمٌ عَلَيۡكُمۡ إِخۡرَاجُهُمۡۚ أَفَتُؤۡمِنُونَ بِبَعۡضِ ٱلۡكِتَٰبِ
وَتَكۡفُرُونَ بِبَعۡضٖۚ فَمَا جَزَآءُ مَن يَفۡعَلُ ذَٰلِكَ مِنكُمۡ إِلَّا خِزۡيٞ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۖ وَيَوۡمَ
ٱلۡقِيَٰمَةِ يُرَدُّونَ إِلَىٰٓ أَشَدِّ ٱلۡعَذَابِۗ وَمَا ٱللَّهُ بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعۡمَلُونَ ٨٥ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱشۡتَرَوُاْ
ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا بِٱلۡأٓخِرَةِۖ فَلَا يُخَفَّفُ عَنۡهُمُ ٱلۡعَذَابُ وَلَا هُمۡ يُنصَرُونَ ٨٦

**83-86.** (የኢስራኢል-ልጆችን)፡- «አላህን እንጂ ሌላን አትገዙ (አታምልኩ)። ለወላጆችም በጎን ስራ ስሩ። ለዝምድና ባለቤቶች፤ ለየቲሞችና ለሚስኪኖችም* በጎን ዋሉ። ለሰዎችም ሁሉ መልካምን ብቻ ተናገሩ። ሶላትን ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ። ዘካን ለተገቢው ስጡ» በማለት ጥብቅ ቃልኪዳን በያዝንባቸው ጊዜ የሆነውን አስታውሱ። ከዚያም ከናንተ ጥቂቶቹ ሲቀሩ ሸሻችሁ። እናንተ (ቃልኪዳንንም) የምትተው ናችሁ። (እናንተ የኢስራኢል ልጆች ሆይ!) የሕዝቦቻችሁን ደም አታፍስሱ። ወገኖቻችሁን ከመኖሪያ አገሮቻቸው አታስወጡ በማለት የጠበቀ ቃልኪዳናችሁን በያዝንባቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውሱ)። ከዚያም በቃል ኪዳኑ ትክክለኛነት አፀናችሁ።

እናንተም በዚሁም ትመሰክራላችሁ፡፡ ከዚያም (ቃል ኪዳናችሁን በማፍረስ) የምትገድሉ፤ ከናንተም መካከል የሆኑ ሕዝቦችን በኃጢአትና በመበደል ላይ በመተባበር ከአገሮቻቸው የምታስወጡ እናንተው ራሳችሁ ናችሁ፡፡ ምርኮኞች ሆነው ወደ እናንተ ሲመጡም ቤዛ (ካሳ) ትከፍላላችሁ፡፡ (ነገሩ) እነርሱን ከመኖሪያ ክልላቸው ማባረሩ በእናንተ ላይ የተከለከለ ነው፡፡ በመፅሐፉ በከፊል አምናችሁ በሌላው ትክዳላችሁን? ከናንተ መካከል ይህንን ፀያፍ ተግባር የሚሰራ ሰው ሁሉ ቅጣቱ በቅርቢቱ ሕይወት ውርደት አንጂ ሌላ አይደለም፡፡ በትንሳኤ ቀንም ወደ ብርቱ ቅጣት ይመለሳሉ፡፡ አላህ የምትሰሩትን ስራ ሁሉ ዘንጊ አይደለም፡፡ እነዚህ እነዚያ ሰዎች ቅርቢቱን ሕይወት በመጨረሻይቱ ሀገር የገዙ (የለወጡ) ሰዎች ናቸው፡፡ ከእነርሱ ላይም ቅጣቱ ምንጊዜም አይቀልላቸውም፡፡ እነርሱም እርዳታም ከማንም አያገኙም፡፡

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሚስኪን ማለት በየሰዎች ዘንድ በመሄድ እንዲያጎርሱት ወይም እንዲመግቡት የሚጠይቅ ሰው ሳይሆን ፍላጎቱን የሚያብቃቃበት ምንም ነገር የሌለውና ሁኔታው በሌሎች ዘንድ የማይታወቅ፤ ሰዎች አንዳች ነገር በምፅዋትነት የማይሰጡትና ፈፅሞ ሰዎችን የማይለምን ሰው ነው»

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ وَقَفَّيْنَا مِنۢ بَعْدِهِۦ بِٱلرُّسُلِ ۖ وَءَاتَيْنَا عِيسَى ٱبْنَ مَرْيَمَ ٱلْبَيِّنَٰتِ وَأَيَّدْنَٰهُ بِرُوحِ ٱلْقُدُسِ ۗ أَفَكُلَّمَا جَآءَكُمْ رَسُولٌۢ بِمَا لَا تَهْوَىٰٓ أَنفُسُكُمُ ٱسْتَكْبَرْتُمْ فَفَرِيقًا كَذَّبْتُمْ وَفَرِيقًا تَقْتُلُونَ ﴿٨٧﴾

87. ለሙሳ መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው፡፡ ከርሱ በኋላም ሌሎች መልዕክተኞችን ልከናል፡፡ የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልፅ ተዐምራትን ሰጠነው፡፡ በቅዱስ መንፈስ (በጅብሪል) በሚባለው መላአክ አበረታነው፡፡ ነፍሶቻችሁ በማትወደው ነገር መልዕክተኛው በመጣላችሁ ቁጥር እነርሱን ከመከተል ይልቅ በትዕቢት ከፊሉን አስተባበላችሁ፡፡ ከፊሉን ደግሞ ትገድላላችሁን፡፡

وَقَالُوا۟ قُلُوبُنَا غُلْفٌۢ ۚ بَل لَّعَنَهُمُ ٱللَّهُ بِكُفْرِهِمْ فَقَلِيلًا مَّا يُؤْمِنُونَ ﴿٨٨﴾ وَلَمَّا جَآءَهُمْ كِتَٰبٌ مِّنْ عِندِ ٱللَّهِ مُصَدِّقٌ لِّمَا مَعَهُمْ وَكَانُوا۟ مِن قَبْلُ يَسْتَفْتِحُونَ عَلَى ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ فَلَمَّا جَآءَهُم مَّا عَرَفُوا۟ كَفَرُوا۟ بِهِۦ ۚ فَلَعْنَةُ ٱللَّهِ عَلَى ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٨٩﴾ بِئْسَمَا ٱشْتَرَوْا۟ بِهِۦٓ أَنفُسَهُمْ أَن يَكْفُرُوا۟ بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بَغْيًا أَن يُنَزِّلَ ٱللَّهُ مِن فَضْلِهِۦ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ ۖ فَبَآءُو بِغَضَبٍ عَلَىٰ غَضَبٍ ۚ وَلِلْكَٰفِرِينَ عَذَابٌ مُّهِينٌ ﴿٩٠﴾

**88-90.** ልቦቻችንም ድፍኖች ናቸው አሉ። እውነታው ግን ይህ አይደለም። አላህ በክህደታቸው ምክንያት ረገማቸው እምነታቸው አናሳ ነው*[1]። ከእነርሱ ጋር ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭ የሆነ መጽሐፍ ከአላህ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ ከመምጣቱ በፊት በእነዚያ በካዱት ላይ ይረዱበት*[2] የነበሩ ሲሆኑ ያ ቀድሞውኑ ያወቁት ነገር በመጣላቸው ጊዜ በእርሱ ካዱ፤ የአላህም እርግማን በካሐዲያን ላይ ይሁን። ነፍሶቻቸውን የሸጡበት (የለወጡበት) ነገር ከፋ! ይኸውም አላህ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ችሮታውን ማውረዱን በመመቅኘት አላህ ባወረደው ነገር መካዳቸው ነው። በቁጣ ላይ ቁጣ አትርፈዋል። ለካሐዲያንም አዋራጅ ቅጣት አለባቸው (ተዘጋጅቶላቸዋል)።

*1 (ትንሽን እንጂ አያምኑም) በማለትም ተተርጉሟል።

*2 «አቡ ቀታደህ እንደሚሉት እኛ አንሷሮች በጃሂሊያ ዘመን ጣዖት አምላኪዎች ሁነን በአይሁድ ላይ የበላይነት ነበረን። እናም እነሱ «አንድ በመጨረሻ ዘመን የሚላክ ነብይ አለ። ዘመኑ ቀርቧል እሱ ሲላክ ከእሱ ጋር ሁነን የዓድና የኢረም ህዝቦችን ቅጣት ነው የምንቀጣችሁ ይሉ ነበር። ከዚያም ቀኑ ደርሶ ሲላኩ ግን ምንም እንደማያውቁ ሁነው ካዱ»ያሉት ነው። (ጦበሪና ኢብኑ ከሲር)።

وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ ءَامِنُواْ بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ قَالُواْ نُؤْمِنُ بِمَآ أُنزِلَ عَلَيْنَا وَيَكْفُرُونَ بِمَا وَرَآءَهُۥ وَهُوَ
ٱلْحَقُّ مُصَدِّقًا لِّمَا مَعَهُمْ ۗ قُلْ فَلِمَ تَقْتُلُونَ أَنۢبِيَآءَ ٱللَّهِ مِن قَبْلُ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿٩١﴾ ۞
وَلَقَدْ جَآءَكُم مُّوسَىٰ بِٱلْبَيِّنَٰتِ ثُمَّ ٱتَّخَذْتُمُ ٱلْعِجْلَ مِنۢ بَعْدِهِۦ وَأَنتُمْ ظَٰلِمُونَ ﴿٩٢﴾ وَإِذْ أَخَذْنَا
مِيثَٰقَكُمْ وَرَفَعْنَا فَوْقَكُمُ ٱلطُّورَ خُذُواْ مَآ ءَاتَيْنَٰكُم بِقُوَّةٍ وَٱسْمَعُواْ ۖ قَالُواْ سَمِعْنَا وَعَصَيْنَا
وَأُشْرِبُواْ فِى قُلُوبِهِمُ ٱلْعِجْلَ بِكُفْرِهِمْ ۚ قُلْ بِئْسَمَا يَأْمُرُكُم بِهِۦٓ إِيمَٰنُكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿٩٣﴾

**91-93.** «አላህ ባወረደው ሁሉ ለእነርሱ እመኑ» በተባሉ ጊዜ በእኛ ላይ«በተወረደው መጽሐፍ ብቻ እናምናለን» ይላሉ። ከእርሱ ኋላ የመጣው ቁርኣን በእኛ ላይ ምንም እንኳን ከእነርሱ ጋር ላለው መጽሐፍ አረጋጋጭና ትክክለኛ የሆነ ቢሆንም ይክዳሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ትክክለኛ አማኞች ከሆናችሁ ከአሁን በፊት የአላህን ነብያት ለምን ገደላችሁ? በላቸው። ሙሳ በግልፅ መረጃ ታጅቦ ወደ እናንተ መጥቶ ነበር። ግን እርሱ በሌለበት ወይፈንን አምላክ አድርጋችሁ ያዛችሁ። አጥፊዎች ነበራችሁ። የጡርን ጋራ ከበላያችሁ በማንሳት በኦሪት ሕግ እንድትሰሩ ቃል ኪዳናችሁን በያዝን ጊዜ (የሆነውን አስታውሱ)። የሰጠናችሁን በጽናት ያዙ ያልነውንም ስሙም አልን። ሰማን ግን አመፅን አሉ። የወይፈኑም ውዴታ በክህደታቸው ምክንያት በልቦቻቸው ውስጥ ገብቷል። ትክክለኛ አማኞች እንደሆናችሁ እምነታችሁ የሚያዝችሁ ነገር የከፋ ነው! በላቸው።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (72-93) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩ የተመረጡ የአላህ መልዕክተኛ ነብይ እንደነበሩ፤
2. አይሁድ በነብዩ ዳዕዋው ላይ ሲያደርሱ የነበረው ተቃውሞ በቀደምትም ነብያት ላይ ሲፈፅሙት የነበረ መሆኑን፤
3. የአይሁድ ጨካኝነት ስር የሰደደ መሰረት ያለው መሆኑን፤
4. እውነትን በማስተባበልና እያወቁ በክህደት መስመር ላይ የፀና አቋም በመያዙ ረገድ አይሁድ ግንባር ቀደም መሆናቸውን፤
5. እውነትን ከልብ እያወቁ በትዕቢትና በማን አለብኝነት ከውሸትና ክህደት ጎራ መሰለፍ እጅግ የዘቀጠ ባህሪ መሆኑን፤
6. አላህ መልካም ስሞችና ምርጥ ባህሪያት እንዳሉት አለማወቅ በራሱ መሀይምነት እንደሆነ፤
7. መፅሐፉን ከላይ ከላይ በማንበብ ብቻ አስተምህሮቶችን እስካልተረዳ ድረስ አዋቂ ተብሎ ሊሰየም እንደማይችል፤
8. እምነት ለሁለቱም ዐለም ተድላ ብቸኛ ቁልፍ በመሆኑ ያለ ማወላወል በልባችን ሊገባ የሚያስፈልግ ጉዳይ መሆኑን፤
9. ለምድራዊ ጥቅሞች ሲባል የሚሰጡ ህገ ወጥ ብያኔዎች ህብረተሰቡን ወደ ብልሹ ስነ ምግባር ውስጥ የሚከቱ መሆናቸዉን፤
10. የትንሳኤ ቀን ዝምድናን ተገን አድርጎ ተጠቃሚ መሆን የማይቻል መሆኑን፤
11. በተስተካከለ እምነትና መልካም ተግባርን በመሰነቅ ከቅጣት ነፃ መውጣትና አስደሳች የሆነውን የጀነት ፀጋ ለመጎናፀፍ እንደሚያበቃ ተገንዝቦ እምነትን ከልብ ማሳደርና ለመልካም ስራዎች መሽቀዳደም እንደሚያስፈልግ፤
12. ለሰዎች ምድራዊ አኼራዊ ጠቀሜታ የሚሰጡ ነገሮችን በሙሉ ማስታወሱ ተገቢ ስለመሆኑ፤
13. ለወላጆች፤ ለዘመዶች፤ ወላጅ አባታቸውን ላጡ እና ረዳት የለሽ ለሆኑ ድሆች ሁሉ መልካም መዋል ተገቢ እንደሆነ፤
14. በኢስላም ለስሜታችን ብቻ የተስማማውን ድንጋጌ ተቀብሎ ከፊሉን ድንጋጌ አለመቀበል ለቅጣት እንደሚያጋልጥ፤
15. የኢስላምን ድንጋጌዎች በሙሉ ልብ ተቀብሎ ያለምንም ማወላወል ለተግባራዊነቱ ራስን ማዘጋጀት ግዴታ መሆኑን፤
16. ለአላህ ፀጋ ምስጋና ማቅረብ ግዴታ እንደሆነና የእርሱን ህግጋት መጣስ ወንጀል መስራት መሆኑ፤
17. ስሜትን በመከተል ከእውነት ማፈንገጥ ወንጀል መሆኑን፤
18. ክቡር የሆነውን የሰው ልጅን ነፍስ ማጥፋት ከፍተኛ ከሆኑ ወንጀሎች አንዱ እንደሆነ፤
19. በእውቀት መመካትና መኩራራት እንዲሁም ከሌላው ለመቀበል አለመዘጋጀት የሚያስከትለውን አደጋ፤ መሆኑን
20. የምቀኝነት ስሜት የሚያደርሰውን ጥፋትና ከብልሹ ባህሪያት አንዱ መሆኑን፤
21. ለመጨረሻ ውድቀት የሚያበቁ መጥፎ ባህሪያት ምን ምን እንደሆኑ፤
22. ወንጀለኞች በይፋ ወንጀልን ሲዳፈሩና በጥፋት ላይ ጥፋትን ሲያስፋፉ በዝምታ መመልከት እንደማይገባ፤
23. ወንጀለኛውን ከወንጀሉ እንዲታቀብ መገሰፅና ከዚያም እንደ ሁኔታው ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም ተገቢ መሆኑን፤
24. አይሁድ የነብያትን ዳዕዋ ለማደናቀፍ እንኳ ወደ ኋላ የማይሉ እንደነበሩ፤
25. ትክክለኛ እምነት ከልብ የመነጨ ሲሆን በኩፍር የተበከለ እምነት ግን ለመጥፎ ተግባር እንደሚገፋፋ እንማራለን።

قُلْ إِن كَانَتْ لَكُمُ ٱلدَّارُ ٱلْـَٔاخِرَةُ عِندَ ٱللَّهِ خَالِصَةً مِّن دُونِ ٱلنَّاسِ فَتَمَنَّوُا۟ ٱلْمَوْتَ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٩٤﴾ وَلَن يَتَمَنَّوْهُ أَبَدًۢا بِمَا قَدَّمَتْ أَيْدِيهِمْ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌۢ بِٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٩٥﴾ وَلَتَجِدَنَّهُمْ أَحْرَصَ ٱلنَّاسِ عَلَىٰ حَيَوٰةٍ وَمِنَ ٱلَّذِينَ أَشْرَكُوا۟ ۚ يَوَدُّ أَحَدُهُمْ لَوْ يُعَمَّرُ أَلْفَ سَنَةٍ وَمَا هُوَ بِمُزَحْزِحِهِۦ مِنَ ٱلْعَذَابِ أَن يُعَمَّرَ ۗ وَٱللَّهُ بَصِيرٌۢ بِمَا يَعْمَلُونَ ﴿٩٦﴾

**94-96.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለአይሁድ የመጨረሻይቱ አገር (ገነት) በአላህ ዘንድ ሌሎች ወገኖች የማይጋሯችሁና ለእናንተ ብቻ በመሆኗ እውነተኞች ከሆናችሁ እስቲ ሞትን ተመኙ በላቸው። እጆቻቸው (ባሳለፉት) በሰሩት ወንጀል ምክንያት ሞትን ምንጊዜም ፈፅሞ አይመኙትም። አላህ በዳዩችን አዋቂ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (አይሁድ) ከሰዎች ሁሉ እና ከእነዚያ ጣኦትን በአላህ ካጋሩት ይበልጥ በሕይወት ላይ የሚጓጉ ሆነው በእርግጥ ታገኛቸዋለህ። ለአንዳቸው ብቻ አንድ ሺህ ዓመት ዕድሜ ቢሰጥ ይወዳል። እርሱም ዕድሜ መሰጠቱ ከቅጣት የሚያድነው አይደለም። አላህ (አይሁድ) የሚሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

ከላሟ ምዕራፍ ከ (94-96) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አይሁዳውያኑ አይሁድ ያልሆነ ሰው ጀነት አይገባም ይላሉ። ይህን ዘረኛ አስተሳሰባቸውን ለማስተባበል ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። እናም አቋማቸው ትክክል መሆኑን ከልባቸው የሚያምኑበት ከሆነ ሞትን እንዲመኙ ተጠይቀዋል ግን አልፈፀሙትም። ሞትን ጠይቀው በነበር አላህ ያከስማቸው ነበር። (ጦበሪ)

قُلْ مَن كَانَ عَدُوًّا لِّجِبْرِيلَ فَإِنَّهُۥ نَزَّلَهُۥ عَلَىٰ قَلْبِكَ بِإِذْنِ ٱللَّهِ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ وَهُدًى وَبُشْرَىٰ لِلْمُؤْمِنِينَ ﴿٩٧﴾ مَن كَانَ عَدُوًّا لِّلَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَرُسُلِهِۦ وَجِبْرِيلَ وَمِيكَىٰلَ فَإِنَّ ٱللَّهَ عَدُوٌّ لِّلْكَٰفِرِينَ ﴿٩٨﴾

**97-98.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለመልዐኩ ጅብሪል ጠላት የሆነ ሰው ሁሉ (ግልፅ ከሃዲ ነው)። (ማወቅ ያለብህ) ከርሱ በፊት የወረዱ መጽሐፍትን የሚያረጋግጡ ለምዕመናን መሪና ብስራት ነጋሪ ሲሆን በአላህ ፈቃድ በልብህ ላይ አውርዶታል። ለአላህና ለመላዕክቱ፤ እንዲሁም ለመልዕክተኞቹም፤ ለጅብሪልና ለሚካኤልም ጠላት የሆነ ሰው ሁሉ (ግልፅ ከሐዲ ነው)። አላህ ደግሞ ለከሐዲያን ጠላት ነው።

ከላሟ ምዕራፍ ከ (97-98) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ዐብደላህ ቢን ሰላም የነብዩን ወደ መዲና መድረስ ሲሰሙ «ነብይ ካልሆነ በስተቀር ማንም የማያውቃቸውን ሶስት ነገሮችን እጠይቅሀለሁ በማለት የሚከተሉትን ጥያቄዎች አቀረቡ።

1. ኛ. ከቂያማ ቀን ምልክቶች የመጀመሪያው ምልክት ምንድን ነው?
2. ኛ. የጀነት ሰዎች የሚመገቡት የመጀመሪያ ምግባቸው ምንድን ነው?
3. ኛ ልጅን ከእናት ጋር ወይም ከአባት ጋር የሚያመሳስለው በምንድ ነው? ነብዩም እነዚህን ነገሮች አሁኑኑ ጅብሪል መጥቶ ነገረኝ በማለት አንድ በአንድ መለሱላቸው። ይሁንና አይሁዶች ጅብሪልማ የአይሁድ ጠላት ነው በማለታቸው ይህን አንቀፅ አነበቡላቸው። የሚለውን አባባል ኢብኑሐጀር የተባሉ ዓሊም አውስተዋል ትክክለኛው ግን አይሁዶች ነብዩን ሶስት ነገሮችን ጠይቀው በነበረበት ወቅት የወረደ አንቀፅ ነው የሚለውን በርካታ ምሁራን ደግፈውታል። ይህንን ገለፃ ኢብኑጀሪር የተባሉት የተፍሲር ሊቅም መርጠውታል። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَلَقَدْ أَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ءَايَٰتٍۭ بَيِّنَٰتٍ ۖ وَمَا يَكْفُرُ بِهَآ إِلَّا ٱلْفَٰسِقُونَ ﴿٩٩﴾
أَوَكُلَّمَا عَٰهَدُوا۟ عَهْدًا نَّبَذَهُۥ فَرِيقٌ مِّنْهُم ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٠٠﴾

**99-100.** ወደ አንተ ግልፅ የሆነ (አንቀፆችን) መመሪያዎችን በእርግጥ አውርደናል። እነርሱንም አመፀኞች እንጂ ሌላው ሰው አይክድም። ቃልኪዳን በገቡ ቁጥር ከነርሱ መካከል ከፊሉ ቃል ኪዳኑን ይጥለዋልን? (ያፈርሰዋልን?)። ይልቁንም አብዛሀኞቻቸው አያምኑም።

ከላሟ ምዕራፍ (99) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ዐብዱላህ ቢን ሱሪያ የተባለ አይሁድ ወደ ነብዩ መጥቶ ምንም የምናውቀው ነገር አላመጣህም ግልፅ የሆነ ነገርም አላሳየኸንም በማለቱ ለእርሱ መልስ ይሆን ዘንድ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

ከላሟ ምዕራፍ (100) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ማሊክ ኢብኑ ሰይፍ ነብዩ በተላኩበትና አይሁዶችን ቃል ያስገባቸውን ሲነገረው በፍፁም ስለ ሙሐመድ በእኛ ላይ ቃል አልተያዘም በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَلَمَّا جَآءَهُمْ رَسُولٌ مِّنْ عِندِ ٱللَّهِ مُصَدِّقٌ لِّمَا مَعَهُمْ نَبَذَ فَرِيقٌ مِّنَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ
كِتَٰبَ ٱللَّهِ وَرَآءَ ظُهُورِهِمْ كَأَنَّهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٠١﴾ وَٱتَّبَعُوا۟ مَا تَتْلُوا۟ ٱلشَّيَٰطِينُ عَلَىٰ مُلْكِ
سُلَيْمَٰنَ ۖ وَمَا كَفَرَ سُلَيْمَٰنُ وَلَٰكِنَّ ٱلشَّيَٰطِينَ كَفَرُوا۟ يُعَلِّمُونَ ٱلنَّاسَ ٱلسِّحْرَ وَمَآ أُنزِلَ
عَلَى ٱلْمَلَكَيْنِ بِبَابِلَ هَٰرُوتَ وَمَٰرُوتَ ۚ وَمَا يُعَلِّمَانِ مِنْ أَحَدٍ حَتَّىٰ يَقُولَآ إِنَّمَا نَحْنُ فِتْنَةٌ
فَلَا تَكْفُرْ ۖ فَيَتَعَلَّمُونَ مِنْهُمَا مَا يُفَرِّقُونَ بِهِۦ بَيْنَ ٱلْمَرْءِ وَزَوْجِهِۦ ۚ وَمَا هُم بِضَآرِّينَ بِهِۦ
مِنْ أَحَدٍ إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ وَيَتَعَلَّمُونَ مَا يَضُرُّهُمْ وَلَا يَنفَعُهُمْ ۚ وَلَقَدْ عَلِمُوا۟ لَمَنِ ٱشْتَرَىٰهُ مَا
لَهُۥ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنْ خَلَٰقٍ ۚ وَلَبِئْسَ مَا شَرَوْا۟ بِهِۦٓ أَنفُسَهُمْ ۚ لَوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ﴿١٠٢﴾ وَلَوْ أَنَّهُمْ
ءَامَنُوا۟ وَٱتَّقَوْا۟ لَمَثُوبَةٌ مِّنْ عِندِ ٱللَّهِ خَيْرٌ ۖ لَّوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ﴿١٠٣﴾

**101-103.** ከነርሱ ጋር ያለን መጽሐፍ የሚያረጋግጥ መልዕክተኛ ከአላህ ዘንድ ተልኮ በመጣላቸው ጊዜ ከእነዚያው መፅሐፍት ከተሰጣቸው ወገኖች ከፊሎቹ ምንም እንደማያውቁ ሆነው የአላህን መጽሐፍ ወደ ኋላቸው ወረወሩት (ጣሉት)። (እነዚያ የአላህን መጽሐፍ አንቀበልም ያሉ አይሁዶች)፤ ሰይጣናት በሱለይማን ዘመነ መንግስት የሚያነቡትን ድግምት ተከተሉ። ሱለይማን ጌታውን አልካደም። ድግምተኛም አልነበረም። ሰይጣናት ግን ሰዎችን ድግምትን የሚያስተምሩ ሲሆኑ በጌታቸው ካዱ። እንደዚሁም አይሁድ በባቢሎን (በባቢል) በሁለቱ መላዕክት በሀሩትና በማሩት ላይ የተወረደውን ነገር ተከተሉ። ሀሩትና ማሩት ግን እኛ ለእናንተ መፈተኛዎች ነንና በጌታህ አትካድ እስከሚሉ ድረስ አንድንም ሰው አያስተምሩም ነበር። ሰዎች ከነርሱም በባልና በሚስቱ መካከል የሚለዩበትን ነገር ያህል ብቻ ይማራሉ። እነርሱም በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር በርሱ አንድንም አይጎዱም። (ድግምት የሚማሩ ሰዎች ሁሉ) የሚጎዳቸውንና ቅንጣት የማይጠቅማቸውን ትምህርት ይማራሉ። እንደ ጥሩ ነገር የለፋበትና በገንዘብም የገዛው ሰው በመጨረሻይቱ አገር ምንም ዕድል የሌለው መሆኑን በእርግጥ (አይሁዶች) ተገንዝበዋል። ነፍሶቻቸውን በርሱ የሸጡበት ዋጋ ምንኛ ከፋ። የሚያውቁ በሆኑ ኑሮ (ይህን ተግባር ባልተገበሩት ነበር።) (አይሁዶች በአላህ) ባመኑና የከለከለውን በተጠነቀቁ ኖሮ መልካምን በተመነዱ ነበር። የሚያውቁ ቢሆኑ ከአላህ ዘንድ የሚገኘው ምንዳ ነፍሶቻቸውን ከሚሸጡበት በላጭ ነው።

ከላሚ ምዕራፍ አንቀፅ (102-103) ኛ ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሰይጣናት ወደ ሰማይ ተቀጣጥለው በመውጣት አንዲትን እውነት ሲያገኙና በሰዎች ዘንድ ሲታወቅ መቶ ውሸት ይጨምሩና ሕዝቡን ያጭበረብራሉ። ጉዳዩንም በፅሑፍ ያስቀምጣሉ። ነብዩ ሱለይማን ይህን ሲሰሙ አሰባስበው ቀበሩት። እሳቸው ሲሞቱ ሰይጣን በሰው ተመስሎ ወደ ቤተ እስራኢሎች መጥቶ ሱለይማን ሕዝቡን ይመራበትና ያስተዳድርበት የነበረውን ልንገራችሁ ብሎ ሱለይማን የቀበሩትን የሀሰት ሰነድ አሳይቶ አውጥቶ በተነው። የጥንቆላ ትምህርት ተስፋፋ። ነብዩ (ﷺ) ነብዩ ሱለይማን ከአላህ መልዕክተኞች አንዱ መሆናቸውን ሲያስተምሩ የሰሙ አንዳንድ አይሁድ ሙሐመድ ሆይ! የዳውድ ልጅ ሱለይማን ጠንቋይ እንጂ ነብይ አልነበረም በማለታቸው ይህንን ፀያፍ አቋማቸውን በመቃወም የወረዱ የቁርኣን አናቅፅ ናቸው። (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ፤ ሓኪምና ጦበሪ)

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (94-103) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኢስላም የቀጥተኛ ህይወት ብቸኛ እውነተኛ መንገድ መሆኑን፤
2. በአንፃሩም አይሁድነት በተቃራኒው ከእውነት ያፈነገጠ ሃይማኖት መሆኑን፤
3. አይሁዳዊያን ለምድራዊ ህይወት ምቾትና ለረጅም ዓመታት ለመኖር ያላቸው ገደብ የለሽ ጉጉት ምን እንደሚመስል፤
4. አላህ የከሓዲያን ሁሉ ጠላት እንደሆነ፤
5. በየዕለቱ ንሰሃ ማድረግ ከክህደት እንደሚያድን፤
6. አይሁድ በቃላቸው የማይገኙ መሆናቸውን፤

7. ትክክለኛው ተውራት የሰውን ልጅ ወደ መልካም መንገድ ለመምራት ከፈጣሪ ከተወረዱ ቅዱሳን መፃህፍት አንዱ መሆኑን፤
8. የተሟላ ግንዛቤ የማያስይዝ እውቀት ከመጥፎ ስራ የመከላከል ብቃቱ ደካማ መሆኑን፤
9. ተውራት ለነብዩ ሙሳ የወረደ የአላህ መፅሐፍ መሆኑን ቁርአን ያረጋገጠ መሆኑን፤
10. የአሁን ዘመን ሙስሊሞች ቁርአንን ችላ እንዳሉት ሁሉ አይሁዶችም ተውራትን በጊዜው ችላ ብለውት እንደነበር፤
11. ነብዩ ሱለይማን ነብይና ንጉስ እንጂ ጠንቋይና የጥንቆላ አስተማሪ እንዳልነበሩ፤
12. ሰይጣናት ድግምትን ለሰው ልጆች በመግለፅ የተሰወሩ ነገሮችን እንደሚያውቁ ማስመሰላቸውን፤
13. ድግምት እውነታነት ያለውና በሰው ልጅ ህይወት ላይ መጠነኛም ቢሆን ተፅዕኖ እንደሚያሳድር፤
14. አላህ ባሮቹን በፈለገው ነገር በሚፈልገው ሰዓት መፈተን እንደሚችል፤
15. ድግምትን በአላህ ቁርአን የቀየረ ሰው በአላህ ዘንድ ምንም ዕጣ ፈንታ እንደሌለው እንማራለን።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَقُولُواْ رَٰعِنَا وَقُولُواْ ٱنظُرْنَا وَٱسْمَعُواْۗ وَلِلْكَـٰفِرِينَ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿١٠٤﴾
مَّا يَوَدُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَـٰبِ وَلَا ٱلْمُشْرِكِينَ أَن يُنَزَّلَ عَلَيْكُم مِّنْ خَيْرٍ مِّن
رَّبِّكُمْۗ وَٱللَّهُ يَخْتَصُّ بِرَحْمَتِهِۦ مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ ذُو ٱلْفَضْلِ ٱلْعَظِيمِ ﴿١٠٥﴾

**104-105.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሆይ! ለነብዩ ራዒና አትበሉ። ተመልከተን «እንዙርና» በሉ። የምትባሉትን ስሙም። ለካሐዲያን አሳማሚ ቅጣት ተዘጋጅቶላቸዋል። እነዚያ ከመጽሐፍ ባለቤቶችም ሆነ ከአጋሪዎች በአላህ የካዱ ሰዎች በእናንተ ላይ ከጌታችሁ የሆነ መልካም ነገር መወረዱን አይወዱም። አላህ በችሮታው በነብይነት የሚፈልገውን ሰው ይመርጣል። አላህም የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው።

**ከላሚ ምዕራፍ አንቀፅ (104-105) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ:-**

1. ነብዩን (ﷺ) ለማየትና ለማናገር ዕድል ያገኙ ሰዎች ሁሉ ከእርሳቸው ጋር በሚያደርጉት የቃላት ልውውጥ አክብሮትን ለእርሳቸው የሚለግሱና ትህትና የተላበሱ ሆነው መገኘት ግዴታ መሆኑን፤
2. ትህትና ሁልጊዜም ቢሆን በማንኛውም ማህበራዊ ህይወታችን ውስጥ አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
3. ነብዩ (ﷺ) የአላህ መልዕክተኛና የዚህ ህዝብ አስተማሪ ሆነው የተሾሙ መሆናቸውን እንማራለን።

۞ مَا نَنسَخْ مِنْ ءَايَةٍ أَوْ نُنسِهَا نَأْتِ بِخَيْرٍ مِّنْهَآ أَوْ مِثْلِهَآۗ أَلَمْ تَعْلَمْ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ
قَدِيرٌ ﴿١٠٦﴾ أَلَمْ تَعْلَمْ أَنَّ ٱللَّهَ لَهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِۗ وَمَا لَكُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ مِن وَلِىٍّ
وَلَا نَصِيرٍ ﴿١٠٧﴾ أَمْ تُرِيدُونَ أَن تَسْـَٔلُواْ رَسُولَكُمْ كَمَا سُئِلَ مُوسَىٰ مِن قَبْلُۗ وَمَن يَتَبَدَّلِ
ٱلْكُفْرَ بِٱلْإِيمَـٰنِ فَقَدْ ضَلَّ سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ﴿١٠٨﴾

**106-108.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከቁርኣን አናቅፅ መካከል አንዲትን እንኳን ብንሽር ወይም እርሷን ብናስረሳህ ከእርሷ የሚበልጥ ወይም ተመሳሳይዋን እናመጣለን። አላህ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ መሆኑን አላወቅክምን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የሰማያትና የምድር ንግስና ለእርሱ ብቻ መሆኑን እና ለእናንተ ከአላህ ሌላ ወዳጅም ሆነ ረዳት ምንም እንደሌላችሁ አላወቅክምን?። (ሰዎች ሆይ!) ከአሁን በፊት ነብዩ ሙሳ እንደተጠየቀው ዓይነት መልዕክተኛችሁን (ሙሐመድን) ልትጠይቁ ትፈልጋላችሁን? በእምነት ክህደትን የሚለውጥ ሰው ሁሉ ትክክለኛውን መንገድ ከደፈ።

ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (104-106) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክኒያት፡-

1. ራዒና የሚለው ቃል አረቦች ይጠቀሙት የነበረ ቋንቋ ነበር። እናም አይሁድ ዘንድ ደግሞ ቅላጼውን በመቀየር ለስድብ ይጠቀሙበት ነበር። ይህንን ቃል ዐረቦች መጠቀማቸውን ሲመለከቱ ሙሐመድን በይፋ የምንሰድብበት ቃል አገኘን አሉ። ማሊክ ቢንሰይፍና ረፋዓት ቢን ዘይድ የተባሉት አይሁዶች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ራዒና በማለት በአሽሙር ተሳደቡ። አንዳንድ ሙስሊሞችም ይህን ቃል ስድብ መሆኑን ሳያውቁ መጠቀም ሲጀምሩ ተንኮል አዘል ቃል በመሆኑ እንዲጠነቀቁት ለማስተማር የወረደ አንቀፅ ነው። (ጦበሪና ዋሒዲ)
2. ሙስሊሞች ለወዳጆቻቸው አይሁዶች በነብዩ (ﷺ) እመኑ ሲሏቸው ይህ ለእኛ እመኑ የምትሉት ነገር እኮ እኛ ካለንበት የተሻለ ነገር አይደለም ይሏቸው ስለነበር ይህ አንቀፅ (105) ወረደ። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ ና እና ኢብኑ ከሲር)
3. ሙሽሪኮች ነብዩ (ﷺ) አንድን ነገር ተከታዩቹን እንዲፈፅሙ አዝዞ እንደገና ያንኑ እንዳይፈፅሙ ይከለክላቸዋል በማለታቸው ምክንያት አንቀፅ (106) ወረደ። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲርና ሱዩጢ)

وَدَّ كَثِيرٌ مِّنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ لَوْ يَرُدُّونَكُم مِّنۢ بَعْدِ إِيمَٰنِكُمْ كُفَّارًا حَسَدًا مِّنْ عِندِ
أَنفُسِهِم مِّنۢ بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمُ ٱلْحَقُّ ۖ فَٱعْفُوا۟ وَٱصْفَحُوا۟ حَتَّىٰ يَأْتِىَ ٱللَّهُ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ
كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿١٠٩﴾

**109.** ከመጽሐፍ ባለቤቶች መካከል ብዙዎቹ እውነቱ ከተገለፀላቸው በኋላ ከነፍሶቻቸው በሆነው ምቀኝነት ብቻ በመገፋፋት ከእምነታቸው በኋላ ከሐዲያን ሊያደርጓቸው ተመኙ። እናም አላህ ትዕዛዙን እስከሚያመጣ ድረስ ይቅርታ አድርጉ፣ እለፏቸውም። አላህ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነውና።

ከላሚ ምዕራፍ (109) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ ሰዎች ኢስላምን እንዳይቀበሉ ጧት ማታ ሲለፉ በነበሩ የተወሰኑ አይሁዶች ነብዩን (ﷺ) ያስቸግሩ በነበሩት አይሁዶችና ከሓዲያን ምክንያት ነው የወረደው።

وَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ وَمَا تُقَدِّمُواْ لِأَنفُسِكُم مِّنْ خَيْرٍ تَجِدُوهُ عِندَ ٱللَّهِۗ
إِنَّ ٱللَّهَ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿١١٠﴾

**110.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ሶላትን አስተካክላችሁ ስገዱ። ዘካንም ለተገቢዎች ስጡ። ለነፍሶቻችሁም ከበጎ ስራ የምታስቀድሙትን በአላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

وَقَالُواْ لَن يَدْخُلَ ٱلْجَنَّةَ إِلَّا مَن كَانَ هُودًا أَوْ نَصَٰرَىٰۗ تِلْكَ أَمَانِيُّهُمْۗ
قُلْ هَاتُواْ بُرْهَٰنَكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿١١١﴾

**111.** ገነትን አይሁድ ወይም ክርስቲያኖች እንጂ ሌላ ሰው አይገባትም አሉ። ይህች ከንቱ ምኞታቸው ናት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እውነተኞች እንደሆናችሁ እስቲ ማስረጃችሁን አምጡ በላቸው።

بَلَىٰۚ مَنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُۥ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ فَلَهُۥٓ أَجْرُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦ
وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿١١٢﴾

**112.** ጉዳዩ እንደመሰላቸው አይደለም። ይልቁንም በጎ ሰሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ የሰጠ ሰው ሁሉ ለእርሱ በጌታው ዘንድ ምንዳ አለው። በእነርሱም ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው አያዝኑምም።

وَقَالَتِ ٱلْيَهُودُ لَيْسَتِ ٱلنَّصَٰرَىٰ عَلَىٰ شَيْءٍ وَقَالَتِ ٱلنَّصَٰرَىٰ لَيْسَتِ ٱلْيَهُودُ عَلَىٰ شَيْءٍ
وَهُمْ يَتْلُونَ ٱلْكِتَٰبَۗ كَذَٰلِكَ قَالَ ٱلَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ مِثْلَ قَوْلِهِمْۚ فَٱللَّهُ يَحْكُمُ بَيْنَهُمْ يَوْمَ
ٱلْقِيَٰمَةِ فِيمَا كَانُواْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ﴿١١٣﴾

**113.** እነርሱ ሁሉንም መጽሐፉን የሚያነቡ ሲሆን አይሁዶች ክርስቲያኖች በምንም ላይ አይደሉም አሉ። ክርስቲያኖችም አይሁዶች በምንም ላይ አይደሉም አሉ። (ምንም እንኳን አንድ ዓይነት መጽሐፍ እንደሚከተሉ ቢያምኑም) እንደዚሁ እነዚያ የማያውቁት አጋሪዎችም የነሱን ተመሳሳይ ንግግር ተናገሩ። አላህ በዚያ ይለያዩበት በነበሩት ነገር ላይ ሁሉ በትንሳኤ ቀን በመካከላቸው ይፈርዳል።

ከላሟ ምዕራፍ (113) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ክርስቲያኖች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው በነበሩበት ጊዜ ከመዲና አይሁድ ምሁራኖች ጋር ምክክር አድርገው ስለነበር ራፊዕ ኢብኑ ኹዘይመህ የተባለ አይሁድ እናንተ እኮ ምንም አይደላችሁም በማለት በነብዩ ኢሳም ሆነ በመፅሐፋቸው በወንጌል ሲክድ ከነጅራናውያን አንዱ ተነስቶ እናንተ ምንም አይደላችሁም በማለት በነብዩ ሙሳም ሆነ በመፅሐፋቸው በተውራት በመካዱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (106-113) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *አላህ የፈለገውን ህግ የማውጣትና የመሻር ባለ ሙሉ መብት መሆኑን፤*
2. *አላህ ህግጋትን ይለውጥ የነበረው ለመፈፀም ይከብዳቸው የነበሩ ድንጋጌዎችን በማሻሻል ያለውን እዝነት እንደሚያረጋግጥ፤*
3. *አግባብ ያልሆኑ ጥያቄዎችን መጠየቅ ለመማር ካለ ፍላጎት የሚመነጭ ባለ መሆኑ አላስፈላጊ መሆኑን፤*
4. *አላህ ህግጋቶችን በየጊዜው መለዋወጡ በሙስሊሞች ዘንድ ተቀባይነት እንዳለው፤*
5. *የሚሻረው ህግ ነክ እንጂ ታሪክ፤ ተውሒድ እና ዘገባ ነክ ጉዳዩች እንደማይሻሩ፤*
6. *የኢስላም ህግ የሰዎችን ጥቅም ለማስከበር የመጣ በመሆኑ ከአንዱ ህግ ወደ ሌላው መለዋወጡ አዲስ ነገር እንዳልሆነ፤*
7. *አላህ የባለስልጣኖች ሁሉ የበላይ በመሆኑ የደነገገውን ሁሉ አሚን ብሎ መቀበል በሁላችንም ግዴታ ስለመሆኑ፤*
8. *ልክ እንደ አይሁዶች ሙስሊም የሆነ ሰው ለነብዩም ሆነ ለዐሊሞች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን ማቅረብ ተገቢ እንዳልሆነ፤*
9. *አይሁድ የነብዩን (ﷺ) መልዕክተኛነት እያወቀ እንዳይቀበሉ ያገዳቸው በልባቸው ውስጥ ሰርፆ የገባው ምቀኝነት እንደነበር፤*
10. *ጂሃድ ለማድረግ ኢስላማዊ ህግ በሚያዘው መሰረት ቅድመ ሁኔታዎቹ ሲሟሉ ብቻ መሆኑን፤*
11. *አላህ ሁሉንም የሚያውቅ መሆኑን በመገንዘብ ዘወትር ከእርሱ ጋር መንፈሳዊ ቁርኝነትን ማጠናከር እንደሚገባ፤*
12. *ብዙዎች ከኢስላም የራቁት ግንዛቤ አጥተው ሳይሆን ስሜታቸውን በመከተል በመሆኑ አስከፊ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው፤*
13. *ለጀነት ተድላ ለመብቃት ብቸኛው ቁልፍ እምነትና መልካም ስራ እንጂ ምድራዊ ፅጋና ዝና ያለመሆኑን እንማራለን።*

وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن مَّنَعَ مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ أَن يُذْكَرَ فِيهَا ٱسْمُهُۥ وَسَعَىٰ فِى خَرَابِهَآ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ مَا كَانَ
لَهُمْ أَن يَدْخُلُوهَآ إِلَّا خَآئِفِينَ ۚ لَهُمْ فِى ٱلدُّنْيَا خِزْىٌ وَلَهُمْ فِى ٱلْءَاخِرَةِ عَذَابٌ عَظِيمٌ ﴿١١٤﴾

**114.** የአላህን መስጊዶች በውስጣቸው ስሙ እንዳይወሳ ከከለከለና መስጊዶችንም ለማበላሸት ከሮጠ ሰው ይበልጥ ድንበር አላፊ (አጥፊ) ማን ነው? እነዚያ በፍርሃት ተውጠው እንጂ ወደ መስጊዶች ሊገቡ አይገባቸውም ነበር። ለነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት አለባቸው። በመጨረሻይቱ ሀገርም ታላቅ ቅጣት አለባቸው።

ከላሚ ምዕራፍ (114) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ቡኽተነሶር የተባለ የበይተል መቅዲስን መስጊድ ያፈረሰ አምባገነን ከሃዲ ስለነበር ስለ እሱ ታሪክ ለመዘከር ነው የወረደው። (ጦበሪ እና ኢብኑ ከሲር)

وَلِلَّهِ ٱلْمَشْرِقُ وَٱلْمَغْرِبُ ۚ فَأَيْنَمَا تُوَلُّوا۟ فَثَمَّ وَجْهُ ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ وَٰسِعٌ عَلِيمٌ ﴿١١٥﴾

**115.** ምስራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው። በአላህ ትእዛዝ (ፊቶቻችሁን) ለሶላት ወደ የትም አቅጣጫ ብታዞሩ የአላህ ፊት እዚያ ዘንድ ነው። አላህ በእርግጥ ችሮታው ሰፊና ዐዋቂ ነው።

ከላሚ ምዕራፍ (115) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከመካ ወደ መዲና ሲሄዱ ቂብላን ሳይጠብቁ ትርፍ ሶላት ሰግደው ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ) ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመርም አንቀፁ የወረደው በትርፍ ሶላት ምክንያት ነው ብለዋል። ኢብኑ ዐባስ ደግሞ አስሀማ (ነጃሺ) ላይ በተደረገው የጀናዛ ሶላት ምክኒያት የተነሳ ከሶሃቦች መካከል አንዳንዶቹ እኛ እንሰግድበት ወደ ነበረው ቂብላ ላልሰገደ ሰው እንዴት ነው የምንሰግድበት በማለት ሲጠያየቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደ ተብሏል። (ሃኪም፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَقَالُوا۟ ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ وَلَدًا ۗ سُبْحَٰنَهُۥ ۖ بَل لَّهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ كُلٌّ لَّهُۥ قَٰنِتُونَ ﴿١١٦﴾
بَدِيعُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ وَإِذَا قَضَىٰٓ أَمْرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿١١٧﴾

**116-117.** አላህ ልጅ አለው አሉ።* ከሚሉት ጥራት ተገባው። ይልቁንም በሰማይና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ነው። ሁሉም ለእርሱ ታዛዦች ናቸው። ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው። ማንንም ነገር ማስገኘት በፈለገ ጊዜ ለእርሱ የሚለው «ሁን» ነው። ወዲያውም እንዳለው ይሆናል።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ እንዲህ ብሏል፡- «የሰው ልጅ በእኔ ላይ ይዋሻል፤ ቢሆንም እሱ ይህን ለማድረግ መብት የለውም። ዘለፈኝም፤ ቢሆንም እሱ ይህን የማድረግ መብት የለውም። በእኔ ላይ መዋሸቱ እኔ ከዚህ በፊት እንደፈጠርኩት ሁሉ ዳግመኛ እንደምፈጥረው ማስተባበሉ ነው። ዘለፋው ደግሞ እኔ ልጅ እንዳለኝ መናገሩ ነው። ጥራት ለእኔ የተገባ ይሁን፤ እኔ ሚስት ወይም ልጅ ከመያዝ የራቅኩ ነኝ»

ከላሚ ምዕራፍ (116) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁዶ ኡዘይር የአላህ ልጅ ነው፤ ክርስቲያኖች ዒሳ የአላህ ልጅ ነው። የመካ ሰዎችም መላኢኮች የአላህ ሴት ልጆች ናቸው። ስላሉ ለሁሉም መልስ እንዲሆን ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ኢብኑ ከሲር)

وَقَالَ ٱلَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ لَوْلَا يُكَلِّمُنَا ٱللَّهُ أَوْ تَأْتِينَآ ءَايَةٌ ۗ كَذَٰلِكَ قَالَ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِم
مِّثْلَ قَوْلِهِمْ ۘ تَشَٰبَهَتْ قُلُوبُهُمْ ۗ قَدْ بَيَّنَّا ٱلْـَٔايَٰتِ لِقَوْمٍ يُوقِنُونَ ﴿١١٨﴾

**118.** እነዚያም የማያውቁት አንተ መልዕክተኛ ስለመሆንህ አላህ ለምን አያናግረንም? ወይም ለእውነተኛነትህ ታዕምር አታመጣልንም ኖረሯልን? አሉ። እነዚያ ከነርሱ በፊት የነበሩትም ልክ እንደዚሁ ንግግራቸው ብጤ ብለዋል። ልቦቻቸው (በክህደት) ተመሳሰሉ። ለሚያረጋግጡ ህዝቦች አንቀፆችን በእርግጥ አብራርተናል።

ከላሚ ምዕራፍ (118) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሪፋዕ ኢብኑ ኹዘይማ የተባለ አንድ አይሁድ ለነብዩ (ﷺ) የአላህ መልዕክተኛ ከሆንክ እስኪ ያነጋግረንና እንስማው በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

إِنَّآ أَرۡسَلۡنَٰكَ بِٱلۡحَقِّ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗاۖ وَلَا تُسۡـَٔلُ عَنۡ أَصۡحَٰبِ ٱلۡجَحِيمِ ﴿١١٩﴾

**119.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ አብሳሪና አስጠንቃቂ አድርገን በእውነት ላክንህ። ከእሳት ጓዶችም ሁኔታ አትጠየቅም።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (114-119) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መስጂድ የተከበረ የአላህ ቤት በመሆኑ በውስጡ መጥፎ ነገሮችን መስራት ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
2. ከሓዲያን ወደ መስጂድ ዘልቀው እንዳይገቡ ማገድና መስጊድ ከነሱ ጥበቃ ማድረግ እንደሚገባ፤
3. መንገደኛ የሆነ ሰው ግዴታ ያልሆነን ሶላት ያለ ቂብላ እንዲሰገድ ፈቃድ የተሰጠው መሆኑን፤
4. አስገዳጅ ምክንያት ካልተፈጠረ በስተቀር በሶላት ጊዜ ወደ ቂብላ አቅጣጫ ዞሮ መስገድ ከሶላት ግዴታዎች አንዱ መሆኑን፤
5. ከአላህ እውቀት ውጭ የሚከናወን ቅንጣት ያህል እንቅስቃሴ እንደሌለ፤
6. ብዙ ዐሊሞች ካፊሮች ወደ መስጂድ መግባት እንደሌለባቸው ይህን አንቀፅ እንደመረጃ እንደሚጠቅሱ፤
7. በተለያየ ቦታና ጊዜ የሚኖሩ ከሓዲያን ምንም እንኳን የጊዜና የቦታ ርቀት ቢለያያቸውም በባህሪ ተመሳሳይ እንደሆኑ፤
8. ልባቸው በእምነት ያልተገነባ በቁርአን ተዓምራቶች ተጠቃሚ ሊሆኑ እንደማይችሉና ያስተማሪ ኃላፊነት ወደ መልካም ጎዳና ማመላከት እንጂ ማስገደድ አለመሆኑን እንማራለን።

وَلَن تَرۡضَىٰ عَنكَ ٱلۡيَهُودُ وَلَا ٱلنَّصَٰرَىٰ حَتَّىٰ تَتَّبِعَ مِلَّتَهُمۡۗ قُلۡ إِنَّ هُدَى ٱللَّهِ هُوَ ٱلۡهُدَىٰۗ
وَلَئِنِ ٱتَّبَعۡتَ أَهۡوَآءَهُم بَعۡدَ ٱلَّذِي جَآءَكَ مِنَ ٱلۡعِلۡمِ مَا لَكَ مِنَ ٱللَّهِ مِن وَلِيّٖ
وَلَا نَصِيرٍ ﴿١٢٠﴾ ٱلَّذِينَ ءَاتَيۡنَٰهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ يَتۡلُونَهُۥ حَقَّ تِلَاوَتِهِۦٓ أُوْلَٰٓئِكَ يُؤۡمِنُونَ بِهِۦۗ
وَمَن يَكۡفُرۡ بِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ﴿١٢١﴾

**120-121.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አይሁዶችም ሆኑ ክርስቲያኖች የራሳቸውን ሀይማኖታቸውን እስከምትከተል ድረስ ካንተ (ተግባር) ፈፅሞ አይወዱም (አይደሰቱም)። ትክክለኛው መንገድ በእርግጥ የአላህ አመራር ነው በላቸው። ይህ በእንዲህ እንዳለ ትክክለኛ እውቀቱ ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌያቸውን ብትከተል አንተን ከአላህ የሚከላከልልህ ወዳጅም ሆነ ረዳት ምንም የለህም። እነዚያ መጽሐፉን የሰጠናቸው ሰዎች ተገቢ ንባቡን ያነቡታል። በእርሱም ያምናሉ። እነዚያ በእርሱ የሚክዱ ክፍሎች ግን ከሳሪዎች እነርሱ ብቻ ናቸው።

يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَتِيَ ٱلَّتِيٓ أَنۡعَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ وَأَنِّي فَضَّلۡتُكُمۡ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٢٢
وَٱتَّقُواْ يَوۡمٗا لَّا تَجۡزِي نَفۡسٌ عَن نَّفۡسٖ شَيۡـٔٗا وَلَا يُقۡبَلُ مِنۡهَا عَدۡلٞ وَلَا تَنفَعُهَا شَفَٰعَةٞ
وَلَا هُمۡ يُنصَرُونَ ١٢٣

**122-123.** እናንተ የኢስራኢል ልጆች ሆይ! እኔ ያ በእናንተ ላይ የለገስኳቸውን አያሌ ፀጋዎችንና በዘመናችሁ ከነበሩት የዓለማት ሕዝቦች በላይ ያበለጥኳችሁ መሆኔን አስታውሱ። አንዲት አማኝ ነፍስ ለሌላ ከሓዲ ነፍስ ምንንም የማትጠቅምበትን፤ ከእርሷም ቤዛ የማይወሰድበትን፤ ምልጃም ለእርሷ የማትፈይድበትን፣ እነርሱም ከየትም በኩል የማይረዱበትን ቀን ተጠንቀቁ።

۞ وَإِذِ ٱبۡتَلَىٰٓ إِبۡرَٰهِـۧمَ رَبُّهُۥ بِكَلِمَٰتٖ فَأَتَمَّهُنَّۖ قَالَ إِنِّي جَاعِلُكَ لِلنَّاسِ إِمَامٗاۖ
قَالَ وَمِن ذُرِّيَّتِيۖ قَالَ لَا يَنَالُ عَهۡدِي ٱلظَّٰلِمِينَ ١٢٤

**124.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂም ጌታው በትዕዛዛት* በፈተነውና በፈፀማቸው ጊዜ የነበረውን ታሪክ (አስታውስ)። እኔ የሰው ዘር መሪ አድርጌሀላሁ አለው። ከዘሮቼም አድርግ ሲል ጠየቀ። አላህም ኢብራሂም ሆይ!ቃል ኪዳኔ ለኢፍትሀውያን አጥፊዎች ተፈፃሚ አይሆንም አለው።

✴ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «አምስት ተግባራት የኢስላም መገለጫዎች ናቸው። እነሱም፡- ግርዛት፤ የብልት ፀጉርን መላጨት፤ የቀድሞ ቀመስን ፂም ማሳጠር፤ ጥፍርን መቁረጥና የብብት ፀጉርን መንጨት» ኢብኑ ዑመር እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአፍንጫ ፂም አሳጥሩ የፊትን ፂም እንዳለ ተውት»

وَإِذۡ جَعَلۡنَا ٱلۡبَيۡتَ مَثَابَةٗ لِّلنَّاسِ وَأَمۡنٗا وَٱتَّخِذُواْ مِن مَّقَامِ إِبۡرَٰهِـۧمَ مُصَلّٗىۖ وَعَهِدۡنَآ إِلَىٰٓ
إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ أَن طَهِّرَا بَيۡتِيَ لِلطَّآئِفِينَ وَٱلۡعَٰكِفِينَ وَٱلرُّكَّعِ ٱلسُّجُودِ ١٢٥

**125.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቤቱንም (ከዕባን) ለሰዎች መሰባሰቢያና የሰላም ማዕከል ባደረግን ጊዜ የነበረውን ታሪክ (አስታውስ)። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ከኢብራሂም መቆሚያ መስገጃን አድርጉ። ወደ ኢብራሂምና እስማዒልም ቤቴን ለሚዞሩት፤ ለሚጎበኙትና በውስጡም ተቀምጠው ለሚፀልዩት ለአጎንባሾችና ለሰጋጆች ሁሉ አጥሩት ስንል ትዕዛዝ አስተላለፍን።

ከላሚ ምዕራፍ (125) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ዑመር ኢብኑ አልኸጣብ ከነበሯቸው ምኞቶች መካከል ከነብዩላሂ ኢብራሂም መቋሚያ ጋር የተያያዘ አንድ ነገር እንዲኖር ይመኙ ስለነበረ ይህን ምኞታቸውን ለማረጋገጥ የወረደ አንቀፅ ነው። (ኢብኑ ከሲር)

وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِـۧمُ رَبِّ ٱجْعَلْ هَـٰذَا بَلَدًا ءَامِنًا وَٱرْزُقْ أَهْلَهُۥ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ
مَنْ ءَامَنَ مِنْهُم بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ ۖ قَالَ وَمَن كَفَرَ فَأُمَتِّعُهُۥ قَلِيلًا
ثُمَّ أَضْطَرُّهُۥٓ إِلَىٰ عَذَابِ ٱلنَّارِ ۖ وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿١٢٦﴾

**126.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂም ጌታዬ ሆይ! ይህንን ሀገር (መካን) ሰላማዊ ሀገር አድርገው። ከኗሪዋም መካከል በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመነውን ክፍል ከፍራፍሬዎች ሲሳይ ስጠው ባለ ጊዜ (የነበረውን ታሪክ) አስታውስ። አላህም የካደውን ሰው በጥቂቱ እንዲጎናፀፍ አደርገዋለሁ። ከዚያ ወደ እሳት ቅጣት እዳርገዋለሁ። ይህም እጅግ አስከፊ ፍፃሜ ነው።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (120-126) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ:-**

1. አይሁድና ክርስቲያኖች የእነርሱን ጎዳና ያልተከተለን ሰው በሙሉ ከልባቸው እንደሚጠሉት፤
2. ቅኑን መንገድ ለማግኘት የፈለገ ማንኛውም ሰው ቁርአንን በትክክል ማንበብና የቁርአንን መመሪያ መከተል እንዳለበት፤
3. የትንሳኤ ቀንን ቅጣት ለመከላከል ጋሻው ጠንካራ እምነት እና መልካም ስራ ብቻ መሆኑን፤
4. በትንሳኤ ዕለት አንዱ ለሌላው ቤዛ ይሆናል ብሎ ማሰብ እንደማያዋጣ፤
5. የህዝብ አስተዳዳሪነት ለመታጨት መስፈርት በልብ ውስጥ ሰርፆ የገባ እምነት እና በዚሁ ላይ የአቋም ፅናት መሆኑን፤
6. ይህ መስፈርት ለማንም ሽምግልና ተብሎ የማይታለፍ መሆኑን፤
7. የህዝበሙስሊሙ አስተዳዳሪ የሆነ ሁሉ ተተኪውን መሪ የማዘጋጀት ግዴታ እንዳለበት፤
8. የአላህን ህግጋት ማክበር ለሌላው ህዝብ ትልቅ አርአያ ለመሆን እንደሚያስችል እንማራለን።

وَإِذۡ يَرۡفَعُ إِبۡرَٰهِـۧمُ ٱلۡقَوَاعِدَ مِنَ ٱلۡبَيۡتِ وَإِسۡمَٰعِيلُ رَبَّنَا تَقَبَّلۡ مِنَّآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلسَّمِيعُ
ٱلۡعَلِيمُ ١٢٧ رَبَّنَا وَٱجۡعَلۡنَا مُسۡلِمَيۡنِ لَكَ وَمِن ذُرِّيَّتِنَآ أُمَّةٗ مُّسۡلِمَةٗ لَّكَ وَأَرِنَا مَنَاسِكَنَا
وَتُبۡ عَلَيۡنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ١٢٨ رَبَّنَا وَٱبۡعَثۡ فِيهِمۡ رَسُولٗا مِّنۡهُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡهِمۡ
ءَايَٰتِكَ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَيُزَكِّيهِمۡۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ١٢٩

**127-129.** ኢብራሂምና ኢስማዒልም ጌታችን ሆይ! ከእኛ ፀሎታችንን ተቀበለን አንተ ሰሚና ዐዋቂ ነህና እያሉ እየፀለዩ የካዕባን ህንፃ (መሰረቶች ግንባታ) ባሳደጉ ጊዜ አስታውስ። ጌታችን ሆይ! ለአንተ ታዛዦች አድርገን። ከዘሮቻችንም ለአንተ ታዛዦች ሕዝቦችን አድርግ። አምልኳዊ ክንውኖችንም አሳውቀን። ንሰሀችንን ተቀበለን። አንተ ፀፀትን ተቀባይና ሩህሩህ አንተ ብቻ ነህና። ጌታችን ሆይ! በውስጣቸው ከእነርሱ የሆነን መልዕክተኛ፤ በእነርሱ ላይ አንቀፆችህን የሚያነብላቸው፤ መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራቸውንም (ከክህደት) የሚያጠራቸውንም ላክላቸው። አሸናፊዉና ጥበበኛው አንተ ብቻ ነህና (የሚሉም ሲሆኑ ከዕባን ገነቡ)።

وَمَن يَرۡغَبُ عَن مِّلَّةِ إِبۡرَٰهِـۧمَ إِلَّا مَن سَفِهَ نَفۡسَهُۥۚ وَلَقَدِ ٱصۡطَفَيۡنَٰهُ فِي ٱلدُّنۡيَاۖ وَإِنَّهُۥ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ
لَمِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ١٣٠ إِذۡ قَالَ لَهُۥ رَبُّهُۥٓ أَسۡلِمۡۖ قَالَ أَسۡلَمۡتُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٣١ وَوَصَّىٰ بِهَآ إِبۡرَٰهِـۧمُ
بَنِيهِ وَيَعۡقُوبُ يَٰبَنِيَّ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰ لَكُمُ ٱلدِّينَ فَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٣٢ أَمۡ كُنتُمۡ
شُهَدَآءَ إِذۡ حَضَرَ يَعۡقُوبَ ٱلۡمَوۡتُ إِذۡ قَالَ لِبَنِيهِ مَا تَعۡبُدُونَ مِنۢ بَعۡدِيۖ قَالُواْ نَعۡبُدُ إِلَٰهَكَ وَإِلَٰهَ
ءَابَآئِكَ إِبۡرَٰهِـۧمَ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗا وَنَحۡنُ لَهُۥ مُسۡلِمُونَ ١٣٣

**130-133.** ከኢብራሂም እምነት ሞኝ ሰው ካልሆነ በስተቀር የሚያፈገፍግ ማን ነው? በቅርቢቱም ዓለም በእርግጥ ለተልዕኳችን መረጥነው። በመጨረሻይቱ ዓለምም እርሱ ከመልካሞቹ ነው። ጌታው ለእርሱ ትዕዛዝ ጠብቅ ባለው ጊዜ ለዓለማት ጌታ ታዝዣለሁ አለ። ኢብራሂምም ልጆቹን በተመሳሳይ አዘዘ። የዕቁብም እንደዚሁ በዚሁ ጉዳይ ልጆቹን አዘዘ። (እንዲህም አለ)፡- ልጆቼ ሆይ! አላህ ለእናንተ ሀይማኖትን መረጠ። ስለዚህ እናንተ ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ እንዳትሞቱ አላቸው። የዕቆብም ለጣዕረ ሞት በተዳረገበት ጊዜ ለልጆቹ ከእኔ በኋላ ምንን ትገዛላችሁ? ባለ ጊዜ ነበራችሁን? እነርሱም አንድ የሆነውን አምላክህንና የአባቶችህን የኢብራሂምን፤ የኢስማዒልንና የኢስሀቅን አምላክ እንገዛለን። እኛ ለእርሱ ፍፁም ታዛዦች ሆነን እናመልከዋለን አሉ።

ከላሟ ምዕራፍ (130) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዐብዱላህ ኢብኑ ሰላም በሰለመ ጊዜ የወንድሙን ልጆች ሰለማንና ሙሀጅርን ኢስላምን እንዲቀበሉ አላህ በተውራት ውስጥ ከእስማኤል ልጆች ስሙ አህመድ የሚባል እልካለሁና ያመነበት ቀናውን መንገድ የያዘ ሲሆን ያላመነ ደግሞ የተረገመ ነው ብሎ ሲያስተምራቸው ሰለማ በምክሩ መሰረት ኢስላምን ሲቀበል ሙሀጅርን ግን እምቢ በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ እና ኢብኑ ከሲር)

ከላሟ ምዕራፍ (133) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁዶች ሙሐመድ ሆይ! ያዕቁብ ሊሞት ሲል ለልጆቹ ይሁዲነትን እንዳትለቁ እንዳለ አታውቅምን? በማለት ሲጠይቋቸው ነው የወረደው። (ጦበሪና ኢብኑ ከሲር)

تِلْكَ أُمَّةٌ قَدْ خَلَتْ ۖ لَهَا مَا كَسَبَتْ وَلَكُم مَّا كَسَبْتُمْ ۖ
وَلَا تُسْأَلُونَ عَمَّا كَانُوا يَعْمَلُونَ ﴿١٣٤﴾

**134.** እኒህ (ከላይ የተወሱት) ህዝቦች በእርግጥ ያለፉ ሕዝቦች ናቸው። ለእነርሱም የስራቸው ምንዳ አላቸው። ለእናንተም የሰራችሁት ስራ ያፈራው (ምንዳ) አላችሁ። እነርሱ ይሰሩት በነበረው ሁሉ ፈፅሞ አትጠየቁም።

وَقَالُوا كُونُوا هُودًا أَوْ نَصَارَىٰ تَهْتَدُوا ۗ قُلْ بَلْ مِلَّةَ إِبْرَاهِيمَ حَنِيفًا ۖ وَمَا كَانَ مِنَ
الْمُشْرِكِينَ ﴿١٣٥﴾ قُولُوا آمَنَّا بِاللَّهِ وَمَا أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَا أُنزِلَ إِلَىٰ إِبْرَاهِيمَ وَإِسْمَاعِيلَ وَإِسْحَاقَ
وَيَعْقُوبَ وَالْأَسْبَاطِ وَمَا أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَمَا أُوتِيَ النَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ
أَحَدٍ مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُ مُسْلِمُونَ ﴿١٣٦﴾

**135-136.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አይሁድና ክርስቲያኖች በየበኩላቸው ቅንን መንገድ ትመሩ ዘንድ አይሁድ ወይም ክርስቲያን ሁኑ አሉ። አይደለም የኢብራሂምን ሀይማኖት ቀጥተኛ ሲሆን እንከተላለን ኢብራሂምም ከአጋሪዎችም አልነበረም በላቸው። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በአላህና ወደ እኛ በተወረደው ቁርኣን ወደ ኢብራሂምም፤ ወደ ኢስማዒልም፤ ወደ ኢስህቅም፤ ወደ የዕቁብና ወደ ነገዶች በተወረደው መለኮታዊ መልዕክት ሁሉ በዚያም ሙሳና ዒሳ በተሰጡት፤ በዚያም ነብያት ሁሉ ከጌታቸው በተለገሱት ከእነርሱ አንዱን ከሌላው የማንለይ ስንሆን አመንን። እኛም ለርሱ (ለአላህ) ታዛዦች ነን በሉ።

ከላሟ ምዕራፍ (135) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-የመዲና አይሁድ አመራሮች እና የነጅራን ክርስቲያን መሪዎች አንዳንዳቸው ለነብዩ (ﷺ) ትክክለኛ መንገድ ማለት እኛ ያለንበት መንገድ ብቻ ነው ይልቁንስ የእኛን መንገድ ብትከተል ይሻልሀል፤ በማለት የራሳቸውን እምነት ሲያደንቁ እውነቱ ምን እንደሆነ ለማስረዳት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከላሟ ምዕራፍ ከ (124-135) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን ውዴታ የሚያስገኘው ትክክለኛ እምነትና መልካም ስራ እንጂ ከትልቅ ዘር መገኘት እንዳልሆነ፤
2. ልጆች አቅማቸው በሚችለው አባቶቻቸውን መርዳት እንዳለባቸው፤
3. ኢስላም ሁሉም ነብያት ለሰው ዘር ያስተማሩት ብቸኛ ሀይማኖት መሆኑን፤
4. ካዕባ ነብዩ ኢብራሂም ከመስራታቸው በፊትም መሠረቱ የነበረና ኢብራሂም ያደረጉት በነበረው መሠረት ላይ መገንባት መሆኑን እንማራለን።

فَإِنْ ءَامَنُوا۟ بِمِثْلِ مَآ ءَامَنتُم بِهِۦ فَقَدِ ٱهْتَدَوا۟ ۖ وَّإِن تَوَلَّوْا۟ فَإِنَّمَا هُمْ فِى شِقَاقٍ ۖ
فَسَيَكْفِيكَهُمُ ٱللَّهُ ۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ١٣٧

**137.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) (አይሁድም ሆነ ክርስቲያኖች) እናንተ ባመናችሁበት ሁሉ ካመኑ በእርግጥ በትክክለኛው ጎዳና ላይ ናቸው። ከእሱ ካፈነገጡ ግን እነርሱ በጭቅጭቅ ውስጥ ብቻ ናቸው። የእነርሱንም ተንኮል አላህ ይበቃሀል። እርሱም የሚሉትን ሰሚና ተግባራቸውን ዐዋቂ ነውና።

صِبْغَةَ ٱللَّهِ ۖ وَمَنْ أَحْسَنُ مِنَ ٱللَّهِ صِبْغَةً ۖ وَنَحْنُ لَهُۥ عَٰبِدُونَ ١٣٨

**138.** የአላህን የተፈጥሮ መንከር (እምነት) ያዙ። በመንከርም ከአላህ ይበልጥ ያማረ ማነው? (ማንም የለም)። እኛም ለእርሱ ብቻ ተገዢዎች ነን (በሉ)።

ከላሟ ምዕራፍ (138) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-ከህዝበ ክርስቲያኑ የተወሰነ ወገን ልጅ ሲወለድለትና ሰባት ቀን ሲሞላው በውሃ ያጠምቁታል። ይህ ለክርስቲያንነቱ ምልክት ነው ብለውም ያምናሉ። ሀሰትነቱን ለማጋለጥ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ ና ኢብኑ ከሲር)

قُلْ أَتُحَآجُّونَنَا فِى ٱللَّهِ وَهُوَ رَبُّنَا وَرَبُّكُمْ وَلَنَآ أَعْمَٰلُنَا وَلَكُمْ أَعْمَٰلُكُمْ وَنَحْنُ لَهُۥ
مُخْلِصُونَ ١٣٩ أَمْ تَقُولُونَ إِنَّ إِبْرَٰهِـۧمَ وَإِسْمَٰعِيلَ وَإِسْحَٰقَ وَيَعْقُوبَ وَٱلْأَسْبَاطَ كَانُوا۟ هُودًا
أَوْ نَصَٰرَىٰ ۗ قُلْ ءَأَنتُمْ أَعْلَمُ أَمِ ٱللَّهُ ۗ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن كَتَمَ شَهَٰدَةً عِندَهُۥ مِنَ ٱللَّهِ ۗ وَمَا ٱللَّهُ
بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعْمَلُونَ ١٤٠ تِلْكَ أُمَّةٌ قَدْ خَلَتْ ۖ لَهَا مَا كَسَبَتْ وَلَكُم مَّا كَسَبْتُمْ ۖ
وَلَا تُسْـَٔلُونَ عَمَّا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ١٤١

**139-141.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ጌታችንና ጌታችሁ ሲሆን ለእኛም ስራችን ያለን ስንሆን ለእናንተም ስራችሁ ያላችሁ ስትሆኑ እኛም ለርሱ ፍፁም ታዛዦች ሆነን ሳለን በአላህ (ሀይማኖት) ትከራከሩናላችሁን?

በላቸው፡፡ ወይም ኢብራሂም፣ ኢስማዒልም፣ ኢስሐቅም፣ የዕቁብም፣ እንዲሁም ነገዶቹም አይሁዶች ወይም ክርስቲያኖች ነበሩ ትላላችሁን? እናንተ ናችሁ የምታውቁት? ወይንስ አላህ? በላቸው፡፡ እርሱም ዘንድ ከአላህ የሆነችን ምስክርነት ከደበቀ ሰው ይበልጥ አጥፊ ማነው? አላህ የምትፈፅሙትን ድርጊት ሁሉ ዘንጊ አይደለም፡፡ እነዚህ በእርግጥ ያለፉ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ለእነርሱ የሰሩት አላቸው፡፡ ለእናንተም የሰራችሁት አላችሁ፡፡ እነርሱ ይሰሩት ከነበሩት አትጠየቁም፡፡

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (136-141) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ**

1. መልካም እድልና ቀና መንገድ ሊገኙ የሚችሉት በኢስላም ጎዳና ስንጓዝ ብቻ መሆኑን፤
2. ከነብያት መካከል ያንዱን ነብይነት ማስተባበል ሁሉንም ነብያት እንደ ማስተባበል እንደሚቆጠር፤
3. አይሁድና ክርስቲያኖች ሁሌም ኢስላምንእንደማይወዱ፡፡
4. አላህን በማምለክ ረገድና በዒባዳ በመጠንከር ፍፁም ሆኖ መገኘት ከፍ ያለ ጥቅምና ክብርን እንደሚያስገኝ፤
5. ሰው በራሱ ስራ እንጂ ሌሎች በሰሩት ኃጢአት ሊቀጣና ሊጠየቅ እንደማይችል፤
6. የግፍ አይነቶች ብዙ መሆናቸውንና እንደየ አይነታቸውም በደረጃ እንደሚበላለጡ እንማራለን፡፡

۞ سَيَقُولُ ٱلسُّفَهَآءُ مِنَ ٱلنَّاسِ مَا وَلَّىٰهُمۡ عَن قِبۡلَتِهِمُ ٱلَّتِي كَانُواْ عَلَيۡهَاۚ
قُل لِّلَّهِ ٱلۡمَشۡرِقُ وَٱلۡمَغۡرِبُۚ يَهۡدِي مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ﴿١٤٢﴾

**142.** *ቂል የህብረተሰብ ክፍሎች ከዚያች በእርሷ ላይ ከነበሩባት ቂብላቸው (አቅጣጫቸው) ምን አዞራቸው? ይላሉ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምስራቁም ምዕራቡም የአላህ ነው፡፡ የሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል በላቸው፡፡

* ክፍል ሁለት

ከላሟ ምዕራፍ (142) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-ነብዩ (ﷺ) መዲና ከሄዱ በኋላ ለአስራ ሰባት ወይም ለአስራ ስድስት ወራት ወደ በይተልመቅዲስ በመዞር ሰግደዋል፡፡ ወደ መካ እንዲዞሩ ሲታዘዙ አይሁዶች ይህንን ምክንያት በማድረግ ኢስላምን በማጣጣላቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ቡኻሪ፤ ሙስሊምና ቲርሚዚ)

وَكَذَٰلِكَ جَعَلۡنَٰكُمۡ أُمَّةٗ وَسَطٗا لِّتَكُونُواْ شُهَدَآءَ عَلَى ٱلنَّاسِ وَيَكُونَ ٱلرَّسُولُ
عَلَيۡكُمۡ شَهِيدٗاۗ وَمَا جَعَلۡنَا ٱلۡقِبۡلَةَ ٱلَّتِي كُنتَ عَلَيۡهَآ إِلَّا لِنَعۡلَمَ مَن يَتَّبِعُ ٱلرَّسُولَ
مِمَّن يَنقَلِبُ عَلَىٰ عَقِبَيۡهِۚ وَإِن كَانَتۡ لَكَبِيرَةً إِلَّا عَلَى ٱلَّذِينَ هَدَى ٱللَّهُۗ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ
لِيُضِيعَ إِيمَٰنَكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِٱلنَّاسِ لَرَءُوفٞ رَّحِيمٞ ﴿١٤٣﴾

**143.** እንደዚሁም (እንደመራናችሁ) ሁሉ በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑና መልዕክተኛውም ሙሐመድ በእናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ምርጥ*1 ማህበረሰብ (ህዝቦች) አደረግናችሁ። ያችንም በእርሷ ላይ የነበርክባትን አቅጣጫ መልዕክተኛውን የሚከተለውን ሰው ወደ ክህደት ከሚመለሰው ሰው ልናውቅ (ልንለይ) (ልንገልፅ) እንጂ ቂብላ አላደረግናትም። እርሷም በዚያ አላህ በመራቸው ሰዎች ላይ በስተቀር በእርግጥ ከባድ ናት። አላህም እምነታችሁን፤ (ስግደታችሁን) የሚያጠፋ አይደለም። አላህ ለሰዎች በጣም ሩህሩህና አዛኝ ነው።*2

*1 ይህንን ክስተት የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) በሰፊው ሲያብራሩት ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒድ አልኹድሪይ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- «በትንሳኤ ቀን ኑሕ ይጠራል «ጌታዬ ሆይ! አቤት» ይላል። አላህም «መልዕክቴን አድርሰሃልን?» ብሎ ይጠይቀዋል። ኑሕም «አዎን» ይለዋል። ከዚያም ሕዝቦቹ «መልዕክቱን አድርሶላችኋልን?»ተብለው ይጠየቃሉ። እነርሱም«ማንም አስጠንቃቂ አልመጣልንም»ይላሉ። አላህም«ለማድረስህ ማን ይመሰክርልሃል?» በማለት ይጠይቀዋል። እሱም«ሙሐመድና ሕዝቦቼ» በማለት ይመልሳል። እነርሱም በእርግጥ መልዕክቱን እንዳደረስ ይመሰክራሉ። መልዕክተኛውም በእናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ ይህም «እንደዚሁም እንደመራናችሁ በሰዎች ላይ መስካሪዎች ልትሆኑና መልዕክተኛውም በናንተ ላይ መስካሪ ይሆን ዘንድ»የሚለው የአላህ ቃል ነው»

*2 ቂብላ ሳይቀየር በፊት የሞቱት ቤተሰቦች ነብዩ ጋር መጥተው ወንድሞቻችን የሞቱት ወደ ቂብላ ሳይሰግድ ነው። ምን ይበጃቸው በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

قَدۡ نَرَىٰ تَقَلُّبَ وَجۡهِكَ فِي ٱلسَّمَآءِۖ فَلَنُوَلِّيَنَّكَ قِبۡلَةٗ تَرۡضَىٰهَاۚ فَوَلِّ وَجۡهَكَ شَطۡرَ ٱلۡمَسۡجِدِ
ٱلۡحَرَامِۚ وَحَيۡثُ مَا كُنتُمۡ فَوَلُّواْ وُجُوهَكُمۡ شَطۡرَهُۥۗ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ لَيَعۡلَمُونَ أَنَّهُ
ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّهِمۡۗ وَمَا ٱللَّهُ بِغَٰفِلٍ عَمَّا يَعۡمَلُونَ ١٤٤ وَلَئِنۡ أَتَيۡتَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ بِكُلِّ
ءَايَةٖ مَّا تَبِعُواْ قِبۡلَتَكَۚ وَمَآ أَنتَ بِتَابِعٖ قِبۡلَتَهُمۡۚ وَمَا بَعۡضُهُم بِتَابِعٖ قِبۡلَةَ بَعۡضٖۚ وَلَئِنِ ٱتَّبَعۡتَ
أَهۡوَآءَهُم مِّنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَكَ مِنَ ٱلۡعِلۡمِ إِنَّكَ إِذٗا لَّمِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٤٥

**144-145.** የፊትህን ወደ ሰማይ መገላበጥ በእርግጥ ተመልክተናል። እናም ወደምትወዳት (ከዕባ) ቂብላ እናዞርልሀለን። ስለዚህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ ወደ ካዕባ አቅጣጫ አዙር። (ሙስሊሞች) የትም ስፍራ ብትሆኑም ስትሰግዱ ፊቶቻችሁን ወደ ካዕባ አቅጣጫ አዙሩ። እነዚያ መጽሐፉን የተሰጡት እርሱ ጌታቸው ሲሆን እውነት መሆኑን ያውቃሉ። አላህ ከምትሰሩት ስራ ዘንጊ አይደለም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነዚያ መጽሐፍን ለተሰጡት ሕዝቦች የምትችለውን ያህል መረጃ ተዐምር ብታቀርብላቸው እንኳ ቂብላህን አይከተሉም። አንተም ቂብላቸውን ተከታይ አይደለህም። ከፊላቸውም የከፊሉን ቂብላ አይከተሉም። ከእውቀትም (ራእይ) ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌያቸውን ብትከተል ያን ጊዜ አንተ ከአጥፊዎች ትደመራለህ (ትሆናለህ)።

ٱلَّذِينَ ءَاتَيۡنَٰهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ يَعۡرِفُونَهُۥ كَمَا يَعۡرِفُونَ أَبۡنَآءَهُمۡۖ وَإِنَّ فَرِيقٗا مِّنۡهُمۡ لَيَكۡتُمُونَ
ٱلۡحَقَّ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ١٤٦ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡمُمۡتَرِينَ ١٤٧

**146-147.** እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው ሰዎች ወንዶች ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ ሁሉ (ሙሐመድን) ያውቁታል። ከእነርሱም የተለዩ ክፍሎች እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑ እውነቱን በእርግጥ ይደብቃሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ ከጌታህ የሆነ እውነት ነው። እናም ከተጠራጣሪዎችም አትሁን።

ከላሟ ምዕራፍ (146) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-ዐብዱላህ ኢብኑ ሰላምና መሰሎቻቸው ማለትም የአይሁድ ምሁራን የነበሩና የሰለሙ ሰዎች አይሁዶች ስለ ነብዩ (ﷺ) የነበራቸውን እውቀት ሲገልፁ ከልጆቻቸው የበለጠ ያውቋቸው እንደነበር ለማረጋገጥ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَلِكُلّٖ وِجۡهَةٌ هُوَ مُوَلِّيهَاۖ فَٱسۡتَبِقُواْ ٱلۡخَيۡرَٰتِۚ أَيۡنَ مَا تَكُونُواْ يَأۡتِ بِكُمُ ٱللَّهُ جَمِيعًاۚ
إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ١٤٨

**148.** ለሁሉም ለስግደት ፊታቸዉን የሚያዞሩባት አቅጣጫ አላቸው። ወደ መልካም ስራዎችም ተሽቀዳደሙ የትም ስፍራ ብትሆኑ አላህ ሁላችሁንም ያመጣችኋል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

وَمِنۡ حَيۡثُ خَرَجۡتَ فَوَلِّ وَجۡهَكَ شَطۡرَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِۖ وَإِنَّهُۥ لَلۡحَقُّ مِن رَّبِّكَۗ وَمَا ٱللَّهُ
بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعۡمَلُونَ ١٤٩ وَمِنۡ حَيۡثُ خَرَجۡتَ فَوَلِّ وَجۡهَكَ شَطۡرَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِۚ وَحَيۡثُ
مَا كُنتُمۡ فَوَلُّواْ وُجُوهَكُمۡ شَطۡرَهُۥ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَيۡكُمۡ حُجَّةٌ إِلَّا ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ
مِنۡهُمۡ فَلَا تَخۡشَوۡهُمۡ وَٱخۡشَوۡنِي وَلِأُتِمَّ نِعۡمَتِي عَلَيۡكُمۡ وَلَعَلَّكُمۡ تَهۡتَدُونَ ١٥٠

**149-150.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከየትም ለጉዞ ከወጣህበት ስፍራ ሁነህ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ አቅጣጫ አዙር። እርሱም ከጌታህ የሆነ እርግጠኛ እውነት ነው። አላህም ከምትሰሩት ስራ ሁሉ ዘንጊ አይደለም። (ሙሐመድ ሆይ!) ከየትኛውም ከወጣህበት ስፍራ ፊትህን ወደ ተከበረው መስጊድ አቅጣጫ አዙር። (ሙስሊሞች ሆይ!) በየትም ስፍራ ላይ ብትሆኑ ፊታችሁን ወደ ካዕባ አቅጣጫ አዙሩ። ይህም እነዚያ ራሳቸውን የበደሉት ሙሽሪኮች በእናንተ ላይ መከራከሪያ ነጥብ እንዳይኖራቸው ነው። እናም አትፍሯቸው እኔን ብቻ ፍሩኝ። ይህን ከፈፀማችሁ በእናንተ ላይ ፀጋዬን እንድሞላላችሁና። ወደ እውነትም እንድትመሩ ነው።

كَمَآ أَرۡسَلۡنَا فِيكُمۡ رَسُولٗا مِّنكُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِنَا وَيُزَكِّيكُمۡ
وَيُعَلِّمُكُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَيُعَلِّمُكُم مَّا لَمۡ تَكُونُواْ تَعۡلَمُونَ ١٥١
فَٱذۡكُرُونِيٓ أَذۡكُرۡكُمۡ وَٱشۡكُرُواْ لِي وَلَا تَكۡفُرُونِ ١٥٢

**151-152.** በውስጣችሁ ከናንተ የሆነን በእናንተ ላይ አንቀፆቻችንን የሚያነብላችሁ እና የሚያጠራችሁ መጽሐፍንና ጥበብንም የሚያስተምራችሁ ታውቁት ያልነበራችሁትንም ነገር የሚያሳውቃችሁ የሆነን መልእክተኛ እንደላክን ፀጋን ሞላንላችሁ። አስታውሱኝ* አስታውሳችኋለሁና። አመስግኑኝ አትካዱኝም።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ እንዳስተላለፉት፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) አንድ ነገር ተናገሩ፤ እኔ ሌላ ነገር ተናገርኩኝ። እሳቸው እንዲህ አሉ፡- «ከአላህ ሌላ ያለ ነገር ለአላህ ባላንጣ አድርጎ እየተጣራ የሞተ ሰው ጀሀነም ገባ» እኔ ደግሞ «ከአላህ ሌላ ያለ ነገር ለአላህ ባላንጣ ሳያደርግ የሞተ ጀነት ገባ» አልኩኝ

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱسۡتَعِينُواْ بِٱلصَّبۡرِ وَٱلصَّلَوٰةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٣
وَلَا تَقُولُواْ لِمَن يُقۡتَلُ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ أَمۡوَٰتُۢۚ بَلۡ أَحۡيَآءٞ وَلَٰكِن لَّا تَشۡعُرُونَ ١٥٤
وَلَنَبۡلُوَنَّكُم بِشَيۡءٖ مِّنَ ٱلۡخَوۡفِ وَٱلۡجُوعِ وَنَقۡصٖ مِّنَ ٱلۡأَمۡوَٰلِ وَٱلۡأَنفُسِ وَٱلثَّمَرَٰتِۗ
وَبَشِّرِ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٥٥ ٱلَّذِينَ إِذَآ أَصَٰبَتۡهُم مُّصِيبَةٞ قَالُوٓاْ إِنَّا لِلَّهِ وَإِنَّآ إِلَيۡهِ رَٰجِعُونَ ١٥٦
أُوْلَٰٓئِكَ عَلَيۡهِمۡ صَلَوَٰتٞ مِّن رَّبِّهِمۡ وَرَحۡمَةٞۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُهۡتَدُونَ ١٥٧

**153-157.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በመታገስና በሶላት ጥንካሬን ፈልጉ። አላህ ከታጋሾች ጋር ነውና። በአላህ መንገድ ለሀይማኖቱ የሚገደሉትን ሰዎች ፍፁም ሙታን ናቸው አትበሉ። በእውነቱ ሕያዋን ናቸውና። እናንተ ግን አትገነዘቡትም። ከፍርሀትና ከርሀብም በጥቂት ነገር፤ ከሀብት፤ ከሕይወት፤ ከአዝመራ፤ በመቀነስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን። ታጋሾችንም በገነት አብስር። እነዚያ መከራ በነካካቻቸው ጊዜ እኛ ለአላህ ነን። እኛም ወደ እርሱ ተመላሾች ነን የሚሉትን (አብስር)። እነዚያ በእነርሱ ላይ ከጌታቸው የሆኑ ምህረቶች ችሮታም አሉ። እነርሱም ወደ እውነት ተመሪዎቹ እነርሱ ናቸውና።

۞إِنَّ ٱلصَّفَا وَٱلۡمَرۡوَةَ مِن شَعَآئِرِ ٱللَّهِۖ فَمَنۡ حَجَّ ٱلۡبَيۡتَ أَوِ ٱعۡتَمَرَ
فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِ أَن يَطَّوَّفَ بِهِمَاۚ وَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَإِنَّ ٱللَّهَ شَاكِرٌ عَلِيمٌ ١٥٨

**158.** የሶፋና የመርዋ (ጋራዎች) የአላህን ትዕዛዝ ከመፈፀሚያ ጉልህ ቦታዎች ናቸው። ካዕባን በሐጅ ወይም በዑምራ ስራ ምክኒያት የጎበኘ ሰው ሁሉ በሁለቱ ጋራዎች መካከል በመመላለሱ ምንም ኃጢአት የለበትም። መልካምንም ስራ በፈቃደኝነት የሰራ ሰው ሁሉ አላህ ይመነዳዋል። አላህ አመሰጋኝና አዋቂ ነውና።

ከላሟ ምዕራፍ (158) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንሷሮች መናት ለምትባል ጣኦታቸው ሐጅ ለማድረግ ኢህራም ሲያደርጉ በሶፋና በመርዋ መካከል ጠዋፍ አያደርጉም ነበር። ኢስላም ከመጣ በኋላ ይህ ተግባር ስለከበዳቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሲዩጢ)

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكۡتُمُونَ مَآ أَنزَلۡنَا مِنَ ٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلۡهُدَىٰ مِنۢ بَعۡدِ مَا بَيَّنَّٰهُ لِلنَّاسِ فِي ٱلۡكِتَٰبِ
أُوْلَٰٓئِكَ يَلۡعَنُهُمُ ٱللَّهُ وَيَلۡعَنُهُمُ ٱللَّٰعِنُونَ ١٥٩ إِلَّا ٱلَّذِينَ تَابُواْ وَأَصۡلَحُواْ وَبَيَّنُواْ
فَأُوْلَٰٓئِكَ أَتُوبُ عَلَيۡهِمۡ وَأَنَا ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ١٦٠

**159-160.** እነዚያ (ስለነብዩ ሙሐመድና ሌሎችም) ከአንቀፆችና ቅን መመሪያዎች ያወረድነውን ለሰዎች በመጽሐፍ ከገለፅነው በኋላ የሚደብቁ ሰዎች ሁሉ አላህ ይረግማቸዋል። ረጋሚዎችም ሁሉ ይረግሟቸዋል። እነዚያ ከመደበቅ የተፀፀቱና አካሄዳቸውን ያስተካከሉና የደበቁትን የገለፁ ሲቀሩ። የእነርሱን ፀፀትንማ እቀበላለሁ። እኔም ፀፀትን በጣም ተቀባይ (አዛኝ) ነኝ።

ከላሟ ምዕራፍ (159) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል እና ባልደረቦቹ የአይሁድ ምሁራንን ስለተውራት አንዳንድ ነገሮች እንዲነግሯቸው ጠየቋቸው። በዚህ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፣ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَمَاتُواْ وَهُمۡ كُفَّارٌ أُوْلَٰٓئِكَ عَلَيۡهِمۡ لَعۡنَةُ ٱللَّهِ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ وَٱلنَّاسِ
أَجۡمَعِينَ ١٦١ خَٰلِدِينَ فِيهَا لَا يُخَفَّفُ عَنۡهُمُ ٱلۡعَذَابُ وَلَا هُمۡ يُنظَرُونَ ١٦٢

**161-162.** እነዚያ በአላህ የካዱና በክህደታቸው ላይ እያሉ የሞቱ ሁሉ ሰዎች በእነርሱ ላይ የአላህ፤ የመላዕክትና የመላው የሰው ዘር ሁሉ እርግማን አለባቸው። በውስጧ (በእርግማን ውስጥም) ሁልጊዜ ዘውታሪዎች ሲሆኑ። ቅጣቱ ከእነርሱ አይቃለልም የእፎይታ ጊዜም አይሰጡም።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (153-162) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ እንዲህ ብሏል «ባሪያዬ በጠረጠረኝ ወቅት እኔ እርሱ ዘንድ ነኝ። እኔም ከርሱ ጋር ነኝ። ለብቻው ካስታወሰኝ ለብቻዬ አስታውሰዋለሁ። በሕብረት ካስታወሰኝ በሕብረት ሆኜ አስታውሰዋለሁ። ወደኔ የስንዝር ያህል ከቀረበ እኔ ደግሞ የክንድ ያህል ወደርሱ ወደ እኔ የክንድ ያህል ከቀረበ እኔ ሁለት እጆቹን እንዲዘረጋ እቀርበዋለሁ። በእግር እየተጓዘ ወደኔ ከቀረበ እኔም ድክድክ በማለት እቀርበዋለሁ»

وَإِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ ١٦٣

**163.** (ሰዎች ሆይ!) አምላካችሁም አንድ አምላክ ብቻ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። እርሱ እጅግ በጣም ሩህሩህና በጣም አዛኝ ነው።

إِنَّ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱلۡفُلۡكِ ٱلَّتِي تَجۡرِي فِي ٱلۡبَحۡرِ
بِمَا يَنفَعُ ٱلنَّاسَ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن مَّآءٖ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَا
وَبَثَّ فِيهَا مِن كُلِّ دَآبَّةٖ وَتَصۡرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ وَٱلسَّحَابِ ٱلۡمُسَخَّرِ بَيۡنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ
لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ١٦٤ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَتَّخِذُ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَندَادٗا يُحِبُّونَهُمۡ
كَحُبِّ ٱللَّهِۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَشَدُّ حُبّٗا لِّلَّهِۗ وَلَوۡ يَرَى ٱلَّذِينَ ظَلَمُوٓاْ إِذۡ يَرَوۡنَ ٱلۡعَذَابَ
أَنَّ ٱلۡقُوَّةَ لِلَّهِ جَمِيعٗا وَأَنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعَذَابِ ١٦٥

**164-165.** የሰማያትና የምድር አፈጣጠር፤ የሌሊትና ቀንም መፈራረቅ (መተካካት)፤ ያችም ሰዎችን የሚጠቅም ነገር ተጭና በባህር ላይ የምትንሳፈፈው መርከብ፤ አላህም ከሰማይ ባወረደው ውሃና በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው በማድረጉ በእርሷም ውስጥ ከተንቀሳቃሽ ሁሉ በመበተኑ፤ ንፋሶችንም በየአቅጣጫው የሚያገላብጥ መሆኑ እንዲሁም በሰማይና በምድር ለሚነዳው ዳመና ለሚያውቁ ሕዝቦች በእርግጥ አያሌ ምልክቶች ይስተዋላሉ። ከሰዎች መካከል ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን ጣዖታትን አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አሉ። እነዚያ ያመኑትም አላህን ከምንም በላይ ይወዳሉ። እነዚያም የበደሉት ሰዎች ቅጣትን (በትንሳኤ ቀን) ባዩ ጊዜ ሀይል ሁሉ ለአላህ ብቻ መሆኑንና አላህም ቅጣቱ ብርቱ እንደሆነ ይገነዘባሉ። በዚህች ዐለም ቢያውቁ ኖሮ (ባላንጣዎችን በመያዛቸው በተፀፀቱ ነበር)

إِذۡ تَبَرَّأَ ٱلَّذِينَ ٱتُّبِعُواْ مِنَ ٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُواْ وَرَأَوُاْ ٱلۡعَذَابَ وَتَقَطَّعَتۡ بِهِمُ ٱلۡأَسۡبَابُ ١٦٦
وَقَالَ ٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُواْ لَوۡ أَنَّ لَنَا كَرَّةٗ فَنَتَبَرَّأَ مِنۡهُمۡ كَمَا تَبَرَّءُواْ مِنَّاۗ كَذَٰلِكَ يُرِيهِمُ ٱللَّهُ
أَعۡمَٰلَهُمۡ حَسَرَٰتٍ عَلَيۡهِمۡۖ وَمَا هُم بِخَٰرِجِينَ مِنَ ٱلنَّارِ ١٦٧

**166-167.** እነዚያ አስከታዮች (የሲያልን) ቅጣትን ባዩ ጊዜ ተከታዮቻቸውን ይከዳሉ፤ በእርሱም መካከል የግንኙነት መስመሮች ሁሉ በተቆረጡ ጊዜ የሚሆኑትን ባወቁ ኑሮ በተጸጸቱ ነበር። እነዚያም ተከታዮችም (ጀሌዎቹም)

ለእኛ ወደ ቅርቢቱ ዓለም እንደገና የመመለስ ዕድል ብናገኝ እኛንም እውቅና እንደነፈጉን (እንደካዱን ሁሉ) እኛም እውቅናን እንነፍጋቸው ነበር ይላሉ። እንደዚሁ አላህ ስራዎቻቸውን በእነርሱ ላይ ፀፀቶች አድርጎ ያሳያቸዋል። እነርሱም ለዝንተ-ዓለም ከእሳት ወጪዎች አይደሉም።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ كُلُواْ مِمَّا فِى ٱلْأَرْضِ حَلَـٰلًا طَيِّبًا وَلَا تَتَّبِعُواْ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيْطَـٰنِ ۚ إِنَّهُۥ لَكُمْ
عَدُوٌّ مُّبِينٌ ﴿١٦٨﴾ إِنَّمَا يَأْمُرُكُم بِٱلسُّوٓءِ وَٱلْفَحْشَآءِ وَأَن تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ ﴿١٦٩﴾

**168-169.** ሰዎች ሆይ! በምድር ካለው ነገር የተፈቀደና ጤናማ የሆነን ምግብ ብሉ የሰይጣንንም ዱካዎች (እርምጃዎች) አትከተሉ። እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና። እርሱ የሚያዛችሁ በኃጢአትና በፀያፍ ነገር በአላህም ላይ የማታውቁትን እንድትናገሩ ብቻ ነው።

ከላሚ ምዕራፍ (168) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰቂፍ ኢብኑ ኹዛዓህና አሚር ቢን ሰዕሰዓህ በራሳቸው ላይ በሂራን፤ ሳኢባን፤ ወሲላን እና ሀምም እያሉ ይሰይሟቸው የነበሩትን እንሰሳዎች እርም አድርገው ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ዋሒዲ)

وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱتَّبِعُواْ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ قَالُواْ بَلْ نَتَّبِعُ مَآ أَلْفَيْنَا عَلَيْهِ ءَابَآءَنَآ ۗ
أَوَلَوْ كَانَ ءَابَآؤُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ شَيْـًٔا وَلَا يَهْتَدُونَ ﴿١٧٠﴾ وَمَثَلُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ
كَمَثَلِ ٱلَّذِى يَنْعِقُ بِمَا لَا يَسْمَعُ إِلَّا دُعَآءً وَنِدَآءً ۚ صُمٌّۢ بُكْمٌ عُمْىٌ فَهُمْ لَا يَعْقِلُونَ ﴿١٧١﴾

**170-171.** ለእነርሱም አላህ ያወረደውን ተከተሉ በተባሉ ጊዜ የለም አባቶቻችንን በእርሱ ላይ ያገኘንበትን ነገር ብቻ እንከተላለን ይላሉ። አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና ወደ እውነት የማይመሩም ቢሆኑ (ይከተሏቸዋልን?) የእነዚያም በአላህ የካዱት ሰዎችና ወደ ቅን መንገድ የሚጣራቸው ሰው ምሳሌ ልክ እንደዚያ ድምፅንና ጥሪን እንጂ ሌላን በማይሰማ እንስሳ ላይ እንደሚጮህ (እረኛ) ብጤ ነው። እነርሱ (እውነትን የማይሰሙ) ደንቆሮዎች፤ (ሐቅን የማይናገሩ) ዲዳዎች፤ (ትክክለኛውን መንገድ የማያዩ) እውሮች ናቸው። ምንንም ነገር የሚገነዘቡ የሚያስታውሱ አይደሉም።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُلُواْ مِن طَيِّبَـٰتِ مَا رَزَقْنَـٰكُمْ وَٱشْكُرُواْ لِلَّهِ إِن كُنتُمْ إِيَّاهُ
تَعْبُدُونَ ﴿١٧٢﴾ إِنَّمَا حَرَّمَ عَلَيْكُمُ ٱلْمَيْتَةَ وَٱلدَّمَ وَلَحْمَ ٱلْخِنزِيرِ وَمَآ أُهِلَّ بِهِۦ لِغَيْرِ ٱللَّهِ ۖ
فَمَنِ ٱضْطُرَّ غَيْرَ بَاغٍ وَلَا عَادٍ فَلَآ إِثْمَ عَلَيْهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٧٣﴾

**172-173.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ከሰጠናችሁ ሲሳዮች መካከል ከሐላሉ (ከተፈቀደላችሁ) ጣፋጭ ብቻ ተመገቡ። አላህን በብቸኝነት የምታመልኩት ከሆናችሁ እሱኑ ብቻ አመስግኑት። (አላህ) በእናንተ ላይ እርም ያደረገባችሁ በክትን፣ ደምን፣ የአሳማ ስጋንና ከአላህ ሌላ በሆነ በማንም ስም የታረደን ስጋ ብቻ ነው። ከላይ የተጠቀሱትን ክልክል ነገሮች መብላት ግድ የሆነበት ሰው ችግሩን ለማስወገድ ያክል ብቻ ሽፍታና ወሰን አላፊ ሳይሆን ቢመገብ በእርሱ ላይ ምንም ሀጢአት የለበትም። አላህ መሐሪና አዛኝ ነውና።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكۡتُمُونَ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَيَشۡتَرُونَ بِهِۦ ثَمَنٗا قَلِيلًا أُوْلَٰٓئِكَ مَا يَأۡكُلُونَ
فِي بُطُونِهِمۡ إِلَّا ٱلنَّارَ وَلَا يُكَلِّمُهُمُ ٱللَّهُ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ وَلَا يُزَكِّيهِمۡ وَلَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٌ ١٧٤ أُوْلَٰٓئِكَ
ٱلَّذِينَ ٱشۡتَرَوُاْ ٱلضَّلَٰلَةَ بِٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡعَذَابَ بِٱلۡمَغۡفِرَةِۚ فَمَآ أَصۡبَرَهُمۡ عَلَى ٱلنَّارِ ١٧٥ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ
نَزَّلَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّۗ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ ٱخۡتَلَفُواْ فِي ٱلۡكِتَٰبِ لَفِي شِقَاقِۭ بَعِيدٖ ١٧٦

**174-176.** እነዚያ አላህ ካወረደው መጽሐፍ (የትኛውንም ክፍል) የሚደብቁ፤ በመደበቃቸው ጥቂትን ዋጋ የሚለውጡ፤ በሆዶቻቸው ውስጥ እሳትን እንጂ አይበሉም። አላህም በትንሳኤ ቀን አያናግራቸውም። ከኃጢአት አያጠራቸውምም። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። እነዚህ ሰዎች እነዚያ ስህተትን በቅንነት ቅጣትንም በምህረት የገዙ (የለወጡ) ናቸው። በእሳት ላይ ምን ታጋሽ አደረጋቸው!። ይህ (ቅጣት ተፈፀሚ የሚሆነው) አላህ መጽሐፍን በእውነት ያወረደ በመሆኑና በእሱ በመካዳቸው ነው። እነዚያም በቁርአን የተለያየ አቋም የያዙት ከእውነት በራቀ ውዝግብ ውስጥ ናቸው።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (163-176) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በኢስላማዊ እውቀታቸው የበቃ እውቀት ያላቸው የእውቀት ባለቤቶች ቁርአንና ሀዲስን ተንተርሰው የሚሰጧቸውን ሀሳቦች መቀበሉ የተፈቀደ ስለመሆኑ፤
2. ሁሉም ነገር ላይ የሚከለከሉ መረጃዎች እስካልመጡ ድረስ የተፈቀዱ መሆናቸውን፤ በኢስላም እይታ በተለያየ ዘመን አላህ ለህዝቦቹ መመሪያ እንዲሆኑ፤ ያወረዳቸውን መመሪያዎች መለወጡ የተለመደ ነበር። ሆኖም ከመልዕክተኛው ሙሐመድ ህልፈት በኋላ ግን የህግጋት መለዋወጥ እንዳበቃ፤
3. ጥቃቅን ነገሮችን በማጋነን ችግር ለመፍጠር መሞከር የከሓዲያን መለያ ባህሪ እንደሆነ፤
4. የነብዩ (ﷺ) ሕዝቦች ከቀደምት ነብያት ህዝቦች በሙሉ የበለጠ ማዕረግ እንደተሰጣቸው፤
5. መፈተን ከሙዕሚኖች መለያ ባህሪ አንዱ መሆኑን፤
6. ሳያውቅ ወደ ቂብላ አቅጣጫ ፊቱን ሳያዞር የሰገደ ሰው ምንም ወንጀል እንደሌለበት፤
7. አይሁድ የቂብላን መቀየር ቀድሞውኑ ያውቁ እንደነበርና ተቃውሟቸው ምንም ማስረጃ የሌለው መሆኑን፤

8. ነብዩ (ﷺ) በግልፅ ለመጠየቅ ለአላህ የነበራቸው ክብር ቢከለክላቸውም አላህ የሚመኙትን በማሟላት እንዳስደሰታቸው፤
9. ካዕባ የነብያት አባት የሆኑት የነብዩ ኢብራሂም የሶላት ቂብላ እንደ ነበረ፤
10. የመፅሐፍ ባለቤቶች የቂብላን መቀየር እውነተኛነት ቀድሞውኑ ያውቁ እንደነበርና ያነሱት ጥያቄ ሙስሊሞችን ለመቃወም ብቻ እንደነበረ፤
11. አቅጣጫዎችን የመወሰን ስልጣን የአላህ ብቻ በመሆኑ ከአንዱ ወደ ሌላው መቀየሩን መቃወም እንደማያስፈልግ፤
12. የነብዩ (ﷺ) ኡመቶች የቂያማ ቀን ባለፉት ሕዝቦች ላይ እንዲመሰክሩ ማድረግ ከሁሉም የበለጡና የተመረጡ መሆናቸውን እንደሚያሳይ፤
13. የቂብላ አቅጣጫ መቀየር አማኞችን ከአስመሳዩች ለመለየት ከፍተኛ ሚና እንደነበረው፤
14. መፅሐፍ እንከተላለን ከሚሉት የመፅሐፍ ሰዎች አብዛኞቹ ኢስላምን የካዱት እያወቁ መሆኑን፤
15. ሙስሊሞች ከከሓዲያን ካፊሮች ጋር ሊመሳሰሉ የማይገባ መሆኑን፤
16. በነብዩ (ﷺ) ዘመን ይኖሩ የነበሩ ቀደምት መፃሕፍት ምሁራን የነብዩን ትክክለኛ መልዕክተኛነት በትክክል ያውቁ እንደነበር፤
17. ከትዕቢተኞች ጋር መከራከር ወደ ትክክለኛው ነጥብ የማያደርስ በመሆኑ መከራከሩ አስፈላጊ እንዳልሆነ፤
18. መንፈሳዊ የሆነ ፍራቻ ለአላህ ብቻ የተገባ ሲሆን ፍጡራንን መንፈሳዊ የሆነ ፍራቻ መፍራት የተከለከለ መሆኑን፤
19. አላህ ላደረገልን መጠነ ሰፊ አካላዊ፤ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፀጋዎች ትልቅ ምስጋና ማቅረብ እንደሚገባን፤
20. የኢስላምን መሰረታዊ የእምነትና የዒባዳን አስተምህሮቶች መማር በእያንዳንዱ ሙስሊም ላይ የተጣለ ግዴታ መሆኑን፤
21. አላህ ዘወትር ከህሊናችን ሊጠፉ እንደማይገባና አላህን ከማውሳት መታቀብ በሕይወታችን ላይ አደጋ እንደሚያስከትልብን፤
22. ትዕግስት ከመልካም ስብዕናዎች ዋነኛው ስኬታማ የሕይወት ቁልፍ ነው። በኢስላም ትዕግስት ከፍ ያለ ማዕረግ አለው። የኢስላም ክብር ከፍ ለማድረግ ራሳቸውን መስዋዕት ያደረጉ አላህ ዘንድ ከፍ ያለ ክብር ይሰጣቸዋል።
23. ፈተና በሰው ልጅ ላይ በሙሉ በተለየ መልኩ የሚደርስ በመሆኑ ይህንን በመገንዘብ ፈተናዎችን በትዕግስት ማሳለፍ ከአላህ ከፍተኛ ምንዳ ያስገኛል። ስለሆነም ፈታኝ የሆኑ ክስተቶችን ሲፈጥሩ (ኢና ሊላሂ ወኢና ኢለይሂ ራጂዑን) እኛ የአላህ ነን እኛም ወደ ወደ እርሱ ተመላሾች ነን በማለት አላህ ምንም ነገር የማድረግ ኃይልና መብት ያለው እኛ ደግሞ የሚያመጣውን በሙሉ የመቀበል ግዴታ እንዳለብን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው።
24. ውዴታ ከዒባዳዎች ውስጥ ስለሚካተት በፍፁም ልብ አላህን መውደድና ማፍቀር የእርሱን ወዳጆችም መውደድ ግዴታ ነው።
25. መንፈሳዊ የሆነ ጥልቅ ውዴታን ከአላህ ውጭ ለማንም አካል መስጠት በአላህ ላይ ከማጋራት ይመደባል።
26. የትንሳኤ እለት ምድራዊ ዝምድና፤ የገንዘብ፤ የስራ ግንኙነቶች በሙሉ ዋጋ ቢስ ሆነው እንደሚቆጠሩ በእምነት ላይ የተመሰረቱ ግንኙነቶች በጎ እንደሚሆኑ፤

27. በሽርክ አያሌ ጭፍሮችን ያፈሩ ሁሉ የትንሳኤ ዕለት ከአምላኪዎቻቸው ጋር የከረረ ጠብ ውስጥ እንደሚገቡ፤
28. በበርዘኽ ዓለም ማለትም፡- ከቀብር እስከ ዕለተ ትንሳኤ ድረስ ባለው ጊዜ መደሰትም ሆነ መቀጣት መኖሩን፤
29. ለምድራዊ ሕይወት መጠቀሚያ የሚሆን ሀላል ስራና የገቢ ምንጭ መፈለግ ግዴታ መሆኑን፤
30. የተፈቀደ እና የተከለከለ ነገር የሚባሉት በድንጋጌ መልክ የሚያስቀምጣቸው አላህ ብቻ መሆኑን፤
31. ጥልቅና መንፈሳዊ ያልሆነውን ተፈጥሯዊ ፍቅርና ውዴታ ለሰብአዊ ፍጡራን (ለሚስት፤ ለልጅ፤ ለአባትና ለእናት) እንዲሁም ለነገሮች፤ ለሀገር፤ ለእንስሳትና ቁሳቁስ ማሳየት የተፈቀደ ነው። ሆኖም ለነዚህ ነገሮች የምንሰጠው ፍቅር ኢስላማዊ እምነትንና ህግጋቱን ከመፈፀም የሚያዘናጋን እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚያስፈልግ፤
32. የሰይጣን መንገዶች እጅግ የበዙና በተለያየ አይነት አሳሳች ዘዴዎች የተቀመሩ ስለሆኑ በከፍተኛ ጥንቃቄ በመጓዝ ከእነዚህ ሰይጣናዊ መንገዶች ራስን መቆጠብ ግዴታ መሆኑን፤
33. ከመጥፎ ብልሹ ምግባሮችና ተግባራት መራቅ ግዴታ መሆኑን በሀይማኖት ላይ በቂ እውቀት የሌላቸውን ጥራዝ ነጠቅ ግለሰቦች መከተል አደጋው የከፋ መሆኑን፤ እነሱን ከመከተል መቆጠብ እንደሚገባ፤
34. ነፍስን ማቆየት የሚያስችል ያህል መመገብ ግዴታ ስለመሆኑና ይህን ማድረግ እየቻለ ያልፈፀመ ሁሉ ወንጀለኛ እንደሆነ፤
35. ሶፋና መርዋ የአላህ አምልኮቶች ከሚተገበሩባቸው ቦታዎች ውስጥ እንደሆኑ፤
36. በሶፋና በመርዋ መካከል የሚደረጉ መንፈሳዊ ጉዞዎች ለነብዩ ኢስማኢል እናት ያጋጠማቸውን ታሪካዊ ክስተት ለማስታወስ እንደሆነ፤
37. ሙሽሪኮች በጃሂልያ ዘመን በድንጋዮች ዙሪያ እየተሸሹ ይፈፅሙት የነበረው ፀያፍ ተግባር በሶፋና በመርዋ መካከል ሙስሊሞች ከምናደርገው ተግባር እንደማይከለክለን፤
38. ለሐጅ ፀሎትም ሆነ ለዑምራ የተጓዘ በሶፋና በመርዋ መካከል የተደነገገውን የጉዞ ስርአት መፈፀም ግዴታው መሆኑን፤
39. የሐጅን ወይም የዑምራን ተግባር ደጋግሞ መፈፀም ከእምነት ጥንካሬ መገለጫዎች አንዱ እንደሆነ፤
40. የሐጅን ወይም የዑምራን ፀሎት ለመፈፀም ያሰበ ሰው በሶፋና በመርዋ መካከል መመላለስና መሄድ ግዴታ እንደሆነ፤
41. የአይሁድና የክርስቲያን ምሁራን የነብዩን ባህሪያት የደበቁት ሰዎችን ከእምነት ለማገድ መሆኑን፤
42. እውቀትን መደበቅ ከአላህ የተሰጠን ኃላፊነት አለመወጣት መሆኑን፤
43. እውቀትን ለህዝቦች ማስፋፋት ማስተማር ግዴታ መሆኑን፤
44. ከአላህ ህግጋት አንዷን እንኳን የደበቀ ሰው ለዘላለም እርግማን እንደሚዳረግ፤
45. በዚህ ጥፋት የተጋለጠ ሰው ንሰሃ ሲገባ ቀደም ሲል የጠፋውን ማስተካከልና ያበላሸውን ማረም እንዳለበት፤
46. የአላህ ሀይማኖት የሆነውን ኢስላምን ለሕዝብ የሚያስተምሩ ሰዎች «ከሓዲያን» የሚል በካፊሮች የሚሰነዘርባቸውን ተቃውሞ አስቀድሞ በመገመት ቅድመ ዝግጅት ማድረግና እርምጃዎችን ለመመከት መዘጋጀት ያስፈልጋል።
47. በኢስላም ውስጥ ያልነበሩ አዳዲስ ነገሮችን ፈጥረው የኢስላም መርሆችን እንደሆኑ የሚያስመስሉ ሰዎችን መከተል የተከለከለ ነው። እውቀት ኢስላምን ለመተግበር ብቸኛው ቁልፍ በመሆኑ እውቀትን መፈለግ የሙስሊሞች ግዴታ ነው። እንዲሁም ሀይማኖታዊ ህግጋትን በጥልቀት የሚያውቁት የእውቀት ባለቤቶችን ወይም ምሁራንን እንጂ መሀይም ጥራዝ ነጠቆችን መከተል እንደማይገባ፤

48. ሐላል የምግብና የመጠጥ፤ የአልባሳት አይነቶችና ሌሎችን ቁሳቁሶች መጠቀሙ ከአላህ ፈቃድ የተሰጣቸው ቢሆንም ማባከኑ የተከለከለ መሆኑን፤
49. አላህን ማመስገን ተገቢ ስለ መሆኑ፤
50. ከህጋዊ የአስተራረድ ስርዓት ውጭ የሞቱ እንስሳትን ስጋ መመገብ የተከለከለ መሆኑንና ሆኖም አስገዳጅ ሁኔታ ከተፈጠረ ነፍስን ለማዳን የበከተ የሞተ እንኳን ቢሆን መብላት የተፈቀደ መሆኑን፤
51. ለችግር ጊዜ የተከለከሉ ነገሮችን ሁሉ የችግሩን ያህል መጠቀም እንደሚፈቀድ፤
52. ህግን መተግበር የሁሉም ሙስሊም ኃላፊነት እንደሆነ፤
53. ሌላው ቀርቶ የተገዳይ ዘመዶች ካሳን ከፈለጉ ገዳይና የገዳይ ዘመዶች እንኳን ለህጉ መተግበር መተባባር እንደላባቸውና እንቅፋት መሆን እንደሌላባቸው፤
54. በግድያ ወንጀል ላይ የሚወሰድ እርምጃ ገዳዩን በመግደል መሆኑንና በነፍስ ዋጋ ማለፍ ግን ሁለተኛ አማራጭ እንደሆነ፤
55. ገዳይ ከፍተኛ ወንጀል የፈፀመ ቢሆንም ከእምነቱ እንደማይወጣ፤
56. በግል ጥረት የተገኘን ሀላል ገንዘብ መጠቀም እንደሚቻል፤
57. ሙዕሚኖች ጌታቸው አላህ ለዋለላቸው ውለታ ማመስገን ግዴታ እንዳለባቸው፤
58. አምልኮን በፍፁምነት መተግበር ከትክክለኛ አማኞች ተግባር እንዱ መሆኑን፤
59. አላህ ለባሮቹ ቆሻሻዎችን እርም አድርጎ ሌላውን እንደፈቀደላቸው፤
60. እውነትን እያወቁ መደበቁ ወንጀል መሆኑን፤
61. የሙስሊም ምሁራን እንደ ቀደምት መፃሕፍ ባለቤቶች ከአላህ መንገድ እንዳያፈነግጡ ማስጠንቀቂያ የተላለፈላቸው መሆኑን፤
62. ውይይት የተፈቀደ ቢሆንም ለጭቅጭቅ የሚጋብዙ ክርክሮች ቁርኣንን መሰረት ያደረጉ እንኳን ቢሆኑ የተከለከሉ መሆኑን እንማራለን።

﴿ لَّيْسَ ٱلْبِرَّ أَن تُوَلُّوا۟ وُجُوهَكُمْ قِبَلَ ٱلْمَشْرِقِ وَٱلْمَغْرِبِ وَلَـٰكِنَّ ٱلْبِرَّ مَنْ ءَامَنَ بِٱللَّهِ
وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ وَٱلْمَلَـٰٓئِكَةِ وَٱلْكِتَـٰبِ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ وَءَاتَى ٱلْمَالَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ ذَوِى ٱلْقُرْبَىٰ
وَٱلْيَتَـٰمَىٰ وَٱلْمَسَـٰكِينَ وَٱبْنَ ٱلسَّبِيلِ وَٱلسَّآئِلِينَ وَفِى ٱلرِّقَابِ وَأَقَامَ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَى ٱلزَّكَوٰةَ
وَٱلْمُوفُونَ بِعَهْدِهِمْ إِذَا عَـٰهَدُوا۟ ۖ وَٱلصَّـٰبِرِينَ فِى ٱلْبَأْسَآءِ وَٱلضَّرَّآءِ وَحِينَ ٱلْبَأْسِ ۗ أُو۟لَـٰٓئِكَ
ٱلَّذِينَ صَدَقُوا۟ ۖ وَأُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُتَّقُونَ ﴿١٧٧﴾

**177.** መልካም ስራ ማለት ፊቶቻችሁን ወደ ምስራቅና ምዕራብ አቅጣጫ ማዞር አይደለም። መልካም ስራ የሚገለፀው በአላህ፣ በመጨረሻው ቀን፣ በመላዕክት፣ በመፅሐፍት በነብያት ያመነ፣ ገንዘብን ምንም ያህል የነዋይ (ገንዘብ) ፍቅር ቢኖረውም ለዝምድና ባለቤቶች፣ ለየቲሞችም፤ ለምስኪኖችም፣ ለመንገደኞችም፣ ለለማኞችም፣ ባሪያዎችን ነፃ ለማውጣት የሰጠ፣ ሶላትን ደንቡን ጠብቆ የሰገደና ዘካን የሰጠ ሰው ተግባር ነው። እንዲሁም መልካም

ሰዎች ቃልኪዳን በገቡ ጊዜ ቃልኪዳናቸውን የሚሞሉ በችግር፣ በበሽታና በፍልሚያ ጊዜ ታጋሾችን (እናወድሳለን) እነዚህ እነዚያ እውነትን የያዙ መሆናቸውን በተግባር አረጋግጠዋል። አላህን የሚፈሩም ናቸው።

ከላሟ ምዕራፍ (177) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ሰው ወደ ነብዩ መጥቶ ቢር (በጎ ስራ) ምንድን ነው ብሎ ሲጠይቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ተብሏል። (ኢብኑ አል-ጀውዚ እና ኢብኑ ከሲር)

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلْقِصَاصُ فِى ٱلْقَتْلَى ۖ ٱلْحُرُّ بِٱلْحُرِّ وَٱلْعَبْدُ بِٱلْعَبْدِ
وَٱلْأُنثَىٰ بِٱلْأُنثَىٰ ۚ فَمَنْ عُفِىَ لَهُۥ مِنْ أَخِيهِ شَىْءٌ فَٱتِّبَاعٌۢ بِٱلْمَعْرُوفِ وَأَدَآءٌ إِلَيْهِ بِإِحْسَـٰنٍ ۗ
ذَٰلِكَ تَخْفِيفٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَرَحْمَةٌ ۗ فَمَنِ ٱعْتَدَىٰ بَعْدَ ذَٰلِكَ فَلَهُۥ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿١٧٨﴾
وَلَكُمْ فِى ٱلْقِصَاصِ حَيَوٰةٌ يَـٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَـٰبِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٧٩﴾

**178-179.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ግድያን በተመለከተ አፀፋዊ እርምጃ በእናንተ ላይ ተደንግጓል። ነፃ ሰው በነፃ መግደል፣ ባሪያ በባሪያ መግደል፤ ሴት በሴት መግደል። ከሟች ወንድሙ ደም ትንሽ ነገር እንኳን ምህረት የተደረገለት ሰው በመሃሪው የሟች ወገን ላይ ገዳዩን በመልካም መከታተል ሲኖርበት፣ ምህረት የተደረገለት ገዳይም የነፍስ ዋጋውን ወደርሱ በመልካም አኳኋን መክፈል አለበት። ይህ ከጌታችሁ የሆነ ማቃለልና እዝነት ነው። ከዚህም በኋላ ህግን የተላለፈ ሰው አሳማሚ ቅጣት ይፀናበታል። እናንተ ባለ አእምሮ ሰዎች ሆይ! በአፀፋዊ እርምጃ ህግ ሕይወትን ትጎናፀፋላችሁ። ይህም ግድያን ከመፈፀም ልትጠነቀቁ ዘንድ ነው። (ገዳይን መግደል ተደነገገላችሁ)

ከላሟ ምዕራፍ (178) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከኢስላም በፊት በሁለት የአረብ ጎሳዎች መካከል ብዙ እልቂትን ያስከተለ ጦርነት ተከናውኖ የነበረና አንዱ በሌላው ላይ ሀይል ስለነበረው አሸናፊው በጉልበቱ በመመካት ደካማውን እንደፈለገ ይጨቁን ስለነበር ነው። (ኢብኑ ከሲር እና ቁርጡቢ)

كُتِبَ عَلَيْكُمْ إِذَا حَضَرَ أَحَدَكُمُ ٱلْمَوْتُ إِن تَرَكَ خَيْرًا ٱلْوَصِيَّةُ لِلْوَٰلِدَيْنِ وَٱلْأَقْرَبِينَ
بِٱلْمَعْرُوفِ ۖ حَقًّا عَلَى ٱلْمُتَّقِينَ ﴿١٨٠﴾ فَمَنۢ بَدَّلَهُۥ بَعْدَ مَا سَمِعَهُۥ فَإِنَّمَآ إِثْمُهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ
يُبَدِّلُونَهُۥٓ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿١٨١﴾ فَمَنْ خَافَ مِن مُّوصٍ جَنَفًا أَوْ إِثْمًا فَأَصْلَحَ بَيْنَهُمْ
فَلَآ إِثْمَ عَلَيْهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٨٢﴾

**180-182.** በማንኛውም ላይ ሞት በመጣበት ጊዜና ቀሪ ሀብት ያለው እንደሆነ ለወላጆችና ለቅርብ ዘመዶች በአግባቡ መናዘዝ በእናንተ ላይ ተደንግጓል። ይህ አላህን በሚፈሩ ላይ መፈፀም ያለበት ግዴታ ነው። ኑዛዜውን ከሰማ በኋላ የለወጠ ሰው ኃጢአቱ በእነዚያ በሚለውጡት ላይ ብቻ ነው። አላህ ሰሚ ዐዋቂ ነውና። ከተናዛዥም በኩል በእውነት መዘንበልን ወይም (ከሲሶ በመጨመር) ኃጢአትን የተገነዘበ (ያወቀ) በመካከላቸውም ያስታረቀ ሰው በእርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም። አላህ በጣም መሀሪና በጣም አዛኝ ነውና።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (177-182) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከእምነታዊ ተግባራት መሀከል ከፊሉን ሰርቶና ተቀብሎ ከፊሉን መተው ከእምነት ያወጣል፤
2. አንድ ሙስሊም የእምነት መሰረቶች የሚባሉት ምን ምን እንደሆኑ በዝርዝር መረዳት ይኖርበታል።
3. ሶላትና ዘካ (የግዴታ ምፅዋት) ከዋና ዋናዎቹ የኢስላም መሰረታዊ የአምልኮት ተግባራት ውስጥ ናቸው።
4. በቃል መገኘት ከኢስላም ድንጋጌዎች አንዱ ሲሆን ቃልን በተግባር መከወን ደግሞ ግዴታ ነው።
5. ትዕግስት መቼም የትም ተፈላጊ ከሆኑ የመልካም ስብዕና መገለጫ መልካም ባህሪያት አንዱ ነው። በተለይ ደግሞ በጦርነት ወቅት ታጋሽ መሆን ድልንና ጀነትን በጣምራ የሚያስገኝ ተፈላጊ ቀመም ነው።
6. ምእመናን የአኼራ ተድላና ምርጥ የጀነት ስጦታ ተዘጋጅቶላቸዋል። ፈራሂያን ማለት እነማን እንደሆኑና ከባህሪያታቸው የፈራሂያን መለያ እንደሚታወቅ፤
7. በኢስላም የሰው አካል ማጉደልና ነፍስ ማጥፋት ከባድ ወንጀል በመሆኑ ማንም ሰው ባጠፋው የአካል ክፍልና ነፍስ ልክ በምድር ላይ እያለ ተመሳሳይ ቅጣት እንዲፈፅምበት አላህ ያዛል። ኢስላማዊ ህግ ይህ ሆኖ እያለ ተበዳይ ወይም የተበዳይ ወራሾች በዳዮችን በይቅርታ ማለፍና ካሳ መቀበል ከፈለጉ ህጉ ይፈቅድላቸዋል።
8. የተመሳሳይ ቅጣትን ህግ መተግበር ለወንጀል ቅነሳና ቅሬታን ለማስወገድ ብቸኛው መፍትሄ መሆኑን፤
9. ቅጣቱን ከበዳዩ ውጭ ባሉ አካሎች ላይ መፈፀም የመሀይሞች ተግባር ከመሆኑም በላይ ፍርድን ማዛባትም ነው።
10. ቅጣት ተመሳሳይ የመሆኑ ምክንያት በራሱ ወንጀልን ከመከላከል አኳያ ከፍተኛ ሚና እንዳለው፤
11. ተበዳይ ወይም የተበዳይ ወራሾች በዳዮችን በይቅርታ ማለፍና ካሳ በመቀበል ከተስማሙ መጉላላት የለባቸውም።
12. ተመሳሳይ ቅጣት መፈፀም በሰዎች ዘንድ ከፍተኛ ጥቅም ያለውና ከአላህ የተደነገገ ግዴታ መሆኑን፤
13. የተመሳሳይ ቅጣት ህግን መተግበር በሰዎች መካከል ቅሬታዎችን ይቀንሳል፤ አጥፊዎችንም ያስተምራል፤
14. ተመሳሳይ ቅጣትን መውሰድ ለግለሰቦችም ሆነ ለማህበረሰቡ ደህንነት ዋስትና መሆኑን፤
15. በኢስላም ከገዳይ ሌላ ማንንም መቅጣት ክልክል መሆኑን፤
16. ቅጣት ጎጂ ሳይሆን አስተማሪ እንዲሆን ተመሳሳይ ተመጣጣኝ መሆን እንዳለበት፤
17. የሟች ዘመዶች ገዳይን ይቅር ቢሉትና በነፍስ ዋጋ ቢስማሙ ያለምንም ማጉላላት መክፈል ግዴታው እንደሆነ፤

18. ህጋዊ ወራሾች ውርስን የሚወስዱት በኑዛዜ መሰረት ሳይሆን አላህ ባወጣው በውርስ ስርአት መሰረት መሆን እንዳለበት፤

19. ብዙ ንብረት ያለው ሰው ኑዛዜ ማድረጉ ተገቢ መሆኑንና ኑዛዜን ወደ ተሻለ ነገር መለወጥ የተፈቀደ መሆኑን እንማራለን።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلصِّيَامُ كَمَا كُتِبَ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ
تَتَّقُونَ ١٨٣ أَيَّامٗا مَّعۡدُودَٰتٖۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۚ
وَعَلَى ٱلَّذِينَ يُطِيقُونَهُۥ فِدۡيَةٞ طَعَامُ مِسۡكِينٖۖ فَمَن تَطَوَّعَ خَيۡرٗا فَهُوَ خَيۡرٞ لَّهُۥۚ وَأَن تَصُومُواْ
خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ١٨٤ شَهۡرُ رَمَضَانَ ٱلَّذِيٓ أُنزِلَ فِيهِ ٱلۡقُرۡءَانُ هُدٗى لِّلنَّاسِ
وَبَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡهُدَىٰ وَٱلۡفُرۡقَانِۚ فَمَن شَهِدَ مِنكُمُ ٱلشَّهۡرَ فَلۡيَصُمۡهُۖ وَمَن كَانَ مَرِيضًا أَوۡ عَلَىٰ
سَفَرٖ فَعِدَّةٞ مِّنۡ أَيَّامٍ أُخَرَۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ بِكُمُ ٱلۡيُسۡرَ وَلَا يُرِيدُ بِكُمُ ٱلۡعُسۡرَ وَلِتُكۡمِلُواْ ٱلۡعِدَّةَ
وَلِتُكَبِّرُواْ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَىٰكُمۡ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ١٨٥

**183-185.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ፆም በእነዚያ ከናንተ በፊት በነበሩት (ሕዝቦች) ላይ ግዴታነቱ እንደተፃፈ ሁሉ በእናንተም ላይ ተደነገገ። ልትጠነቀቁ ይከጀላልና። ውስን የሆኑት የረመዷንን ወር ቀናትን ፁሙ። ከናንተም ውስጥ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ባልፆማቸው ቀናት ልክ ተመሳሳይ ቁጥር ያላቸውን ቀናት መፆም አለበት። እነዚያ ለመፆም ከአቅም በላይ ችግር የገጠማቸው ሰዎች ደግሞ አፍጥረው ለየቀኑ እንድ ድሃን የአንድ ጊዜ ምግብ ማብላት ይኖርባቸዋል[*1]። ከዚህ በላይ ቤዛን በመጨመር መልካምንም ስራ የፈቀደ ሰው (እርሱ ፈቅዶ መጨመሩ) ለራሱ በላጭ ተግባር ነው። ግና በመንገድ ላይ ሆናችሁ መፆማችሁ ለእናንተ የበለጠ ነው የምታውቁ ብትሆኑ (ትመርጡታላችሁ)[*2]። (እንድትጾሙት ግዴታ የተደረገባችሁ) ያ በርሱ ውስጥ ለሰዎች መሪ ከቅን መንገድና (እውነትን ከውሸት) ከሚለዩት ገላጮች (አንቀጾች) ሲሆን ቁርአን የተወረደበት የረማዳን ወር ነው። ከናንተ መካከል ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው። በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ካፈጠረ ከሌሎች ቀናት ባልፆማቸው ቀናት ልክ ቁጥሮችን በልኩ መፆም አለበት። አላህ ሁልጊዜም ለእናንተ ገሩን ነገር ይሻል እንጂ። በእናንተ ላይ ጫና መፍጠርን አይሻምና ነው። ይሁንና በተጨማሪም ለፆም የተወሰኑትን ቀናት ልትሞሉና አላህን ቅንኑ መንገድ ስለመራችሁ ልታከብሩትና ልታመሰግኑት ዘንድ (ይህን ደነገገላችሁ)።

*1 መፆምን በግድ የሚችሉ...ተብሎም ተተተርጉሟል። በዚህ አይነቱ ፍች ይህ ህግ ተሽሯል ማለት ነው።

✷2 ይህ አንቀፅ በሚቀጥለው አንቀፅ ተሽሯል። እናም መፆም አማራጭ የሌለው ግዴታ ሁኗል።

ከላሚ ምዕራፍ (184) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙጃሂድ የተባሉት ታላቅ የተፍሲር ምሁር ይህ አንቀፅ የወረደው በአለቃ ቀይስ ቢን ሳብ በተባለው ሶሃባ ምክንያት ሲሆን እሱም የረመዳንን ወር አፍጥሮ ለእያንዳንዱ ቀን አንድ ሚስኪን ስላበላ ነው ብለዋል። (ሱዩጢና እና ቁርጡቢ)

وَإِذَا سَأَلَكَ عِبَادِى عَنِّى فَإِنِّى قَرِيبٌ ۖ أُجِيبُ دَعْوَةَ ٱلدَّاعِ إِذَا دَعَانِ ۖ
فَلْيَسْتَجِيبُوا۟ لِى وَلْيُؤْمِنُوا۟ بِى لَعَلَّهُمْ يَرْشُدُونَ ﴿١٨٦﴾

**186.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባሮቼ ስለ እኔ በጠየቁህ ጊዜ እኔ ቅርብ ነኝ። የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ። ስለዚህ ወደ ቀናው መንገድ ይመሩ ዘንድ✷ ለእኔ ብቻ ይታዘዙ። በእኔም ብቻ ይመኑ በላቸው።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- .... ከጠየቀኝ በርግጥ እሰጠዋለሁ። ከእኔ ጥበቃን ከፈለገ በእርግጥ እጠብቀዋለሁ።»

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (183-186) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በሒጅሪያ አቆጣጠር መሰረት በዋናው 9ኛ ወር ላይ የሚገኘውን የረመዳን ወር መፆም ግዴታ ስለመሆኑ፤
2. ፆም የአላህ ፍራቻን የሚያዳብር ወንጀሎችን የሚያሰርዝ ከዋና ዋና የዒባዳ አይነቶች አንዱ መሆኑን፤
3. ለበሽተኛና መንገደኛ ሰው በረመዳን ወር ፆም ማፍጠር የተፈቀደ መሆኑን፤ ነገር ግን ሰውየው ከበሽታው ከዳነ አሊያም ከጉዞው መጠናቀቅ በኋላ ባፈጠረው ቀን ልክ ቀዷእ (ምትክ) መፆም እንዳለበት፤
4. የረመዳንን ወርና ሰላት ህግጋት ዋነኛ ምንጭ ከሆነው መመሪያችን ቁርአን ጋር ያላቸውን ታሪካዊ ግንኙነትና በአላህ ዘንድ ያለውን ከፍ ያለ ማዕረግ እንዲሁም ታላቅነት፤
5. የረመዳንን ወር መፆም ግዴታ የሚሆንባቸው ሙስሊም የህብረተሰብ ክፍሎች እነማን እንደሆኑ፤
6. በችግር የረመዳንን ወር በሙሉም ሆነ በከፊል ያልፆሙ ችግሩ ሲወገድ ያልፆሟቸውን ቀናት መፆም እንደሚገደዱ፤
7. ህግጋት በማንም ሰው አቅም ሊሰሩ የሚችሉ ተግባራትን የሚደነገጉ መሆናቸውን፤
8. ለበሽተኛ ሰው ፆሙን አፍጥሮ ከረመዳን ውጭ ሲሻለው መፆም የሚችል መሆኑን፤ ነፍሰ ጡርና ጡት የሚያጠቡ እናቶች እንዲሁም አዛውንቶች ፆም ማፍጠር እንደሚችሉ፤
9. ፆም አላህ ለሙስሊሞች ሁሉ የደነገገው መሆኑን፤
10. ፆም የሰዎችን ህይወት ለማፅዳትና ትዕግስትን ለማስተማር ጠቃሚ እንደሆነ፤
11. የረመዷንን ወር ለመፆም የተመረጠው ቁርአን መውረድ የጀመረበት ወር መሆኑን፤
12. ለመፆም ችግር ያለባቸው ሰዎች እንዲያፈጥሩ መፍቀዱ የአላህን ሩህሩህነት እንደሚያመለክት፤
13. የአላህን ህግጋት መተላለፍ ፍፁም የተከለከለ መሆኑን እንገነዘባለን፤
14. አላህ ለፍጡራኖቹ በሙሉ ቅርብና ሰሚ ጌታ ስለሆነ እርሱን ለመለመን ድምፅን ከፍ ባይልም ልዩነት አለመኖሩን፤
15. ፀሎቱ አላህ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው በአላህ በፅኑ ማመን፤ መልካም ስራን መስራት እንዳለበት እንማራለን።

أُحِلَّ لَكُمۡ لَيۡلَةَ ٱلصِّيَامِ ٱلرَّفَثُ إِلَىٰ نِسَآئِكُمۡۚ هُنَّ لِبَاسٞ لَّكُمۡ وَأَنتُمۡ لِبَاسٞ لَّهُنَّۗ عَلِمَ ٱللَّهُ
أَنَّكُمۡ كُنتُمۡ تَخۡتَانُونَ أَنفُسَكُمۡ فَتَابَ عَلَيۡكُمۡ وَعَفَا عَنكُمۡۖ فَٱلۡـَٰٔنَ بَٰشِرُوهُنَّ وَٱبۡتَغُواْ
مَا كَتَبَ ٱللَّهُ لَكُمۡۚ وَكُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكُمُ ٱلۡخَيۡطُ ٱلۡأَبۡيَضُ مِنَ ٱلۡخَيۡطِ ٱلۡأَسۡوَدِ
مِنَ ٱلۡفَجۡرِۖ ثُمَّ أَتِمُّواْ ٱلصِّيَامَ إِلَى ٱلَّيۡلِۚ وَلَا تُبَٰشِرُوهُنَّ وَأَنتُمۡ عَٰكِفُونَ فِي ٱلۡمَسَٰجِدِۗ تِلۡكَ
حُدُودُ ٱللَّهِ فَلَا تَقۡرَبُوهَاۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ ءَايَٰتِهِۦ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَتَّقُونَ ١٨٧

**187.** (ሙስሊሞች ሆይ!) በፆም ሌሊት ከሚስቶቻችሁ ጋር የግብረ ስጋ ግንኙነት ተፈቀደላችሁ። እነርሱ ለእናንተ ልብሶች ናቸው። እናንተም ለእነርሱ ልብሶች ናችሁና። አላህ በዚህ ረገድ ነፍሶቻችሁን በማታለል ላይ መሆናችሁን ያውቃል። ስለዚህ አሁን ልትገናኟቸው ትችላላችሁ። አላህም ለናንተ የፃፈላችሁን ነገር (ልጅ) ፈልጉ። ስላለፈውም ምህርት አድርጎላችኋል። ይቅርም ብሏችኋል። አላህ ነጭ የንጋት ገመድ ከጥቁሩ ለእናንተ እስከሚገለፅላችሁ ድረስ ብሉ። ጠጡም። ከዚያ ፆምን እስከ ሌሊቱ ድረስ ሙሉ። እናንተ በመስጊዶች ተቀማጮች (ኢዕቲካፍ) ላይ ስትሆኑ ግን ሚስቶቻችሁን አትገናኙዋቸው። ይህች የአላህ ህግጋት ናትና ለመተላለፍ አትቅረቧት። እንደዚሁ አላህ አንቀፆችን ለሰዎች ያብራራል። እነርሱ የተከለከሉትን ሊጠነቀቁ ይከጀላልና።

وَلَا تَأۡكُلُوٓاْ أَمۡوَٰلَكُم بَيۡنَكُم بِٱلۡبَٰطِلِ وَتُدۡلُواْ بِهَآ إِلَى ٱلۡحُكَّامِ
لِتَأۡكُلُواْ فَرِيقٗا مِّنۡ أَمۡوَٰلِ ٱلنَّاسِ بِٱلۡإِثۡمِ وَأَنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ١٨٨

**188.** አንዱ ወገን የሌላውን ወገን ገንዘብ በከንቱ (ያለ አግባብ) አትብሉ። ኢፍተሃዊ መሆኑን እያወቃችሁም የሰዎችን ማንኛውንም መብት በግፍ ለመንፈግ (ለመቀማት) ለዳኞች ጉቦ አትስጡ።

ከላሚ ምዕራፍ (188) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- እምሩኡልቀይስ እና አብዳን የተባሉ ሰዎች በመሬት ተጣልተው ወደ ነብዩ (ﷺ) መጡና ተሟገቱ። በጉዳዩ ኢምሩኡልቀይስ መሐላ ሊፈፅም ሲል ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

۞يَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلۡأَهِلَّةِۖ قُلۡ هِيَ مَوَٰقِيتُ لِلنَّاسِ وَٱلۡحَجِّۗ
وَلَيۡسَ ٱلۡبِرُّ بِأَن تَأۡتُواْ ٱلۡبُيُوتَ مِن ظُهُورِهَا وَلَٰكِنَّ ٱلۡبِرَّ مَنِ ٱتَّقَىٰۗ
وَأۡتُواْ ٱلۡبُيُوتَ مِنۡ أَبۡوَٰبِهَاۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ١٨٩

**189.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስለለጋ ጨረቃ (መለዋወጥ) ይጠይቁሃል። ይህ ክስተት ጊዜን ለመለካት የሚጠቀሙበትና የሐጅንም ወቅት ለማወቅ የሚረዳ ምልክት ነው በላቸው። መልካም ስራ ቤቶችን ከጀርባዎቻቸው በመግባታችሁ የሚለካ አይደለም። ይልቁንም የመልካም ስራ ባለቤት አላህን የሚፈራ ሰው ነው። መኖሪያ ቤቶችን በፊት በራቸው በኩል ግቡ። አላህንም ፍሩ። ከጀሀነም ቅጣት ልትድኑ ዘንድ በላቸው።

ከላሟ ምዕራፍ (189) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል ከነብዩ (ﷺ) ዘንድ አይሁዶች በየጊዜው ስለ ጨረቃ አወላለድና እድገት ልክ እንደ ገመድ ሆኖ ይጀምርና እስከሚሞላ ድረስ ያድጋል ከዚያም እንደ ነበር ይመለሳል ለምንድ ነው? እንደ ፀሐይ አንድ አይነት አልሆነም ብለው ይጠይቁናል ብሎ በመናገሩ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (187-189) አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ**

1. በረመዳን ጎህ እስከሚቀድ ድረስ መብላት መጠጣትና የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ የተፈቀደ መሆኑን፤
2. ፆም ማለት ከጎህ መቅደድ አንስቶ እስከ ፀሀይ መጥለቂያ ባለው ጊዜ ከምግብ ከመጠጥና ከግብረ ስጋ ግንኙነት እንዲሁም ከፀያፍ ተግባራትና ንግግር ታቅቦ መዋል እንደሆነ፤
3. መስጊድ ውስጥ መቀመጥ (እዕቲካፍ) ዘወትር ሊፈፀም የሚገባ የኢስላም ድንጋጌ ቢሆንም በተለይ በረመዳን ወር እጅግ ተፈላጊ የዒባዳ አይነት ሲሆን ለተከታታይ ቀናት ኢዕቲካፍ ነይቶ መስጊድ የገባ ሰው ሚስቱን መገናኘት ተገቢ እንዳልሆነ፤
4. በግልፅ ለመናገር የሚያስፈሩ እውነታዎችን በሚያባቡ ስውር ቃላት መጠቀም ተገቢ ስለመሆኑ፤
5. የአላህን ህግጋት በመጣስ በወንጀሎች ክልል ውስጥ መግባት ያለውን አደጋ፤
6. የኢስላም ድንጋጌዎች ክልከላዎችና ገደቦች ዓላማቸው በሙስሊሙ ልብ ውስጥ የአላህን ፍራቻ ለማስረፅ መሆኑን፤
7. የሱሁርን ምግብ መብላት ተገቢ መሆኑን፤
8. የስሁርን ምግብ ማዘግየቱ እንደሚፈለግ፤
9. በረመዳን ሌሊት ጎህ (ፈጅር) ከመውጣቱ በፊት ጀናባ ሆኖ ማንጋት ከአላህ ዘንድ እንደ ማያስጠይቅ፤
10. ኢዕቲካፍ እንደሚገባና እሱም ሊፈፀም የሚችለው በመስጊድ እንደሆነ፤
11. ኢዕቲካፍ በሚታወቁ መስጊዶች ካልሆነ በስተቀር እንደማይሆን፤
12. የግብረ ስጋ ግንኙነት ኢዕቲካፍን እንደሚያበላሽ፤
13. የረመዳን ወር ለፆም የተመረጠበት ምክንያት ቁርኣን የወረደበት በመሆኑ እንደሆነ፤
14. ፆም ባለፉትም ህዝቦች ሙስሊሞች በነበሩ ላይ ግዴታ የነበረ መሆኑን፤
15. ፆም ህይወትን ለማፅዳትና ትዕግስትን ለመማር ታላቅ ትምህርት መሆኑን
16. ኢስላም ለግለሰቦች ንብረት ዋስትና ከፍተኛ ጥበቃ የሚያደርግ ስለ መሆኑ እንንማራለን።

وَقَٰتِلُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَكُمۡ وَلَا تَعۡتَدُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡمُعۡتَدِينَ ١٩٠
وَٱقۡتُلُوهُمۡ حَيۡثُ ثَقِفۡتُمُوهُمۡ وَأَخۡرِجُوهُم مِّنۡ حَيۡثُ أَخۡرَجُوكُمۡۚ وَٱلۡفِتۡنَةُ أَشَدُّ مِنَ ٱلۡقَتۡلِۚ
وَلَا تُقَٰتِلُوهُمۡ عِندَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ حَتَّىٰ يُقَٰتِلُوكُمۡ فِيهِۖ فَإِن قَٰتَلُوكُمۡ فَٱقۡتُلُوهُمۡۗ كَذَٰلِكَ
جَزَآءُ ٱلۡكَٰفِرِينَ ١٩١ فَإِنِ ٱنتَهَوۡاْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ١٩٢ وَقَٰتِلُوهُمۡ حَتَّىٰ لَا تَكُونَ
فِتۡنَةٞ وَيَكُونَ ٱلدِّينُ لِلَّهِۖ فَإِنِ ٱنتَهَوۡاْ فَلَا عُدۡوَٰنَ إِلَّا عَلَى ٱلظَّٰلِمِينَ ١٩٣

**190-193.** (አማኞች ሆይ!) እነዚያን የሚጋደሏችሁን ከሐዲያን በአላህ መንገድ* ተጋደሉ። ነገር ግን ወረራ አትፈፅሙ (ወሰን አትለፉ)። አላህ ወራሪዎችን አይወድምና። ባገኛችኋቸውም ስፍራ ሁሉ ግደሏቸው። ካስወጧችሁም ስፍራ (ከመካ) አስወጧቸው። ስቃይ (ክህደት) ከመግደል የከፋ ነውና። በተከበረው መስጊድም ዘንድ በእርሱ ውስጥ እስከሚጋደሏችሁ ድረስ አትጋደሏቸው። ከተጋደሏዋችሁ ግን ግደሉዋቸው። የከሓዲያን ቅጣት ልክ እንደዚህ ነው። ከውጊያ ከታቀቡ ግን አላህ መሀሪና አዛኝ መሆኑን እወቁ። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ጭቆና (ሁከት) እስኪወገድና ሁሉም ለአላህ እጅ እስኪሰጡ ድረስ ተጋደሏዋቸው። ከታቀቡ ግን የሀይል እርምጃ ወሰንን ባለፉ ላይ እንጂ በሰላማዊ ላይ አይፀናም።

*✷ መስፈርቱ የተሟላ ጂሃድ በኢስላም ከፍተኛ ምንዳ ያለው ቅዱስ ተግባር ነው። ቁርአንም ሐዲስም ይህንኑ ሐቅ ያረጋግጣሉ። ከእነዚህም መካከል አሁን ያለንበት አንቀፅ አንዱ ነው። ከሐዲሶችም መካከል ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደሏህ ብን መስዑድ እንዳስተላለፉት። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! መልካም ሥራዎች የትኞቹ ናቸው?» ስል ጠየቅኳቸው። እሳቸውም «ሶላቶችን በጊዜያቸው መስገድ» አሉኝ «ከዚህ ሌላስ?» ስል ጠየቅኳቸው። «በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግል» ብለው መለሱልኝ። ከዚያ በኋላ የአላህ መልዕክተኛን ሌላ ጥያቄ አልጠየቅኳቸውም። እንደው ተጨማሪ ሌላ ጥያቄዎችን ብጠይቃቸው ኖሮ በርካታ ነገሮች ይነገሩኝ ነበር» ያሉት ነው።*

*ከላሚ ምዕራፍ* **(190-193)** *ያሉትት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በስድስተኛው አመት ሂጅሪያ ላይ ኡምራ ለማድረግ ባልደረቦቻቸውን አስከትለው በመካ የሚታረዱ ስጦታዎችን ይዘው፤ የኡምራ ልብሳቸውን ለብሰው ወደ መካ ጉዟቸውን ቀጠሉ መካውያን የነብዩን (ﷺ) ኡምራ ማድረግ መፍቀድ ቀርቶ ወደ መካ ለመግባት ሙከራ ካደረጉ ጦርነት እንደሚያውጁባቸው ዛቱ። ከዚያም በመካከላቸው በተደረጉ እልህ አስጨራሽ ሽምግልና ለኢስላም ስር ነቀል ለውጥ ማምጣቱ የሚነገርለት ታሪካዊ ስምምነት ተደረገ። የስምምነቱም አናቅፅ የሚከተሉት ነበሩ፡-*

1. *በዚህ አመት ነብዩ (ﷺ) ከሙስሊሞች ጋር ወደ መካ ሳይገቡ ይመለሳሉ በሚቀጥለው አመት ከአፎቱ ያልወጣ ጎራዴ (ሰይፍ) ብቻ ሲቀር ሌላ የጦር መሳሪያ ሳይዙ መካ በመግባት ለሶስት ቀናት ይቆያሉ፤*
2. *በሁለቱም መካከል ለአስር ዓመታት ጦርነት አይካሄድም።*
3. *ከነብዩ ጋር ስምምነት መፍጠር የፈለገ ማንኛውም ወገን መፍጠር ይችላል። እንዲሁም ከቁረይሾች ጋር ስምምነት መፍጠር የፈለገ ማንኛውም ወገን ስምምነት መፍጠር ይችላል፤*

4. ከቁረይሾች ወደ ሙስሊሞች የሸሸን ሰው ሙስሊሞች ወደ ቁረይሾች ይመልሱለታል። ከሙስሊሞች ወደ ቁረይሾች የሸሸውን ሰው ቁረይሾች ወደ ሙስሊሞች አይመልሱትም። (ኢብኑ ከሢር እና ሲዩጢ)

ٱلشَّهۡرُ ٱلۡحَرَامُ بِٱلشَّهۡرِ ٱلۡحَرَامِ وَٱلۡحُرُمَٰتُ قِصَاصٞۚ فَمَنِ ٱعۡتَدَىٰ عَلَيۡكُمۡ فَٱعۡتَدُواْ عَلَيۡهِ بِمِثۡلِ مَا ٱعۡتَدَىٰ عَلَيۡكُمۡۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلۡمُتَّقِينَ ١٩٤

**194.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) የተከበረው ወር በተከበረው ወር አንፃር ነው። ፍትሃዊ አፀፋዊ እርምጃ የተከበረን ህግ በጣሱ ላይ ተደንግጓል። በተከበረው ወር ወሰን ያለፈባችሁን ሰው በእናንተ ላይ ወሰን ባለፈው ብጤ በእርሱ ላይ ወሰን ያለፈውን ያህል በእርሱ ላይ ወሰን እለፉበት። አላህንም ፍሩ። አላህ ከሚፈሩት ጋር መሆኑንም እወቁ።

ከላሟ ምዕራፍ (194) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) እና ባልደረቦቻቸው በስድስተኛ አመት ሂጅሪያ ላይ ተከልክለውት የነበረውን ኡምራ በስምምነቱ መሰረት በሰባተኛ ዓመት ተፈቅዶላቸው ሶስት ቀን በካዕባው ስላሳለፉ አላህ ያሳካላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ የወረደ አንቀፅ ነው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ኢብኑ ከሲር)

وَأَنفِقُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَلَا تُلۡقُواْ بِأَيۡدِيكُمۡ إِلَى ٱلتَّهۡلُكَةِ وَأَحۡسِنُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٩٥

**195.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በአላህ መንገድ ላይ ለግሱ። ራሳችሁን በገዛ እጃችሁ ለጥፋት አትዳርጉ። በበጎ ስራም ላይ ፅኑ። አላህ በጎ ሰሪዎችን ሁሉ ይወዳልና።

ከላሟ ምዕራፍ (195) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የዲኑን መጠናከርና መስፋፋት አይተው በገንዘባቸው ከመታገል ወደ ኋላ ባሉ አንሷሮች ምክንያት ነው። (ዋሒዲ እና ሲዩጢ)

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (190-195) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በኢስላምና በሙስሊም ላይ ጥቃት በመሰንዘር ጦርነትን ቀድሞ ያወጀን የከሓዲያን ጦር መጋደል ግዴታ መሆኑን፤
2. በዘመቻ ወቅት የህፃናት፤ የሽማሌዎችንና የሴቶችን መብት በማክበር ጥቃት እንዳይደርስባቸው መጠንቀቅ ግዴታ መሆኑን፤
3. የጠላት ጦር ገፍቶ ካላጠቃ በስተቀር በተከበረው የአላህ ቤት ክልል (ሀረም) ውስጥ ጦርነት ማድረግ የተከለከለ መሆኑን፤
4. ሙስሊሞችን መጨቆንና ማንገላታት ከመግደል የማይተናነስ መሆኑን፤
5. ጂሃድ የተደነገገው የኢስላም ጠላቶችን ጭቆና ለማቆም፤ በህዝቦች መካከል ችግሮች እንዳይኖሩ ለማድረግና የኢስላማዊ ትምህርት እንደልብ እንዲስፋፋ ለማድረግ መሆኑን፤
6. ኢስላም በማንም ይሁን በማን ጭቆናን እንደማይቀበል፤
7. ኢስላም ሙስሊም ከመሆን በፊት የተሰሩ ወንጀሎችን ባጠቃላይ የሚያስምር መሆኑን፤

8. ሙስሊሞችን የሚጨቁን ህብረተሰብ እስካለ ድረስ ጂሃድ ግዴታ መሆኑን፤
9. በጂሃድ ጊዜም ቢሆን ሴቶችን፤ ህፃናትን፤ ሽማግሌዎችን፤ እብዶችንና መነኮሳትን መግደል ክልክል መሆኑ፤
10. ከዚህም አልፎ በጂሃድ ጊዜ እንስሳትን መግደል፤ ንብረትን ማጥፋት ክልክል ስለ መሆኑ፤
11. ግብር ከፍለው መኖር የሚችሉትንና ግብር ለመክፈል ዝግጁ ሆነውም ያሉትን ከሓዲያን መግደል ክልክል መሆኑን፤
12. ሁለት ችግሮች ሲፈጠሩ ከፍተኛውን ለመቋቋም ዝቅተኛውን መፈፀም ተገቢ መሆኑን፤
13. አላህ ጊዜያትን ለመቁጠሪያ የፈጠራቸው ወራቶች ማዕረግና ክብር እንድንሰጣቸው በአላህ ትዕዛዝ የተሰጠን እንደሆነ፤
14. አላህ ማዕረግና ክብር የሰጣቸውን ወራቶች፤ ቦታዎችንና ነገራቶችን በሙሉ ማክበር አስፈላጊ እንደሆነ፤
15. ጥቃትን በተመሳሳይ ጥቃት መመከት መብት ማስከበር በመሆኑ ተፈላጊ እንደሆነ፤
16. ደግነት ከመልካም ባህሪያት ከፍተኛ ደረጃን እንደሚያጎናፅፍ፤
17. መገዳደል የአላህን ሃይማኖት ለማስከበርና ከልዩ ልዩ መሰናክሎች ለማዳን መሆን እንዳለበት፤
18. አላህ ጭቆናንና በደልን ምንጩ ከየትም ቢሆን እንደሚያወግዘው፤
19. ሙስሊሞችን በመጨቆንና በማሳደድ ማንገላታት ከመግደል እንደማይተናነስ፤
20. ጂሃድ የተደነገገው በሙስሊሞች ላይ የሚደርሱትን ጥቃቶች ከምድረ ገፅ ለማጥፋትና ሰላም ለመፍጠር መሆኑን፤
21. ለጂሃድ በሚደረጉ የሕይወትም ሆነ የገንዘብ መስዋዕትነት አለመሳተፍ እያወቁ እንደማጥፋት እንደሚቆጠር፤
22. ጦርነት ሰዎችን ቢከብዳቸውም እውነትን ለማውጣትና ዲኑን ለማስከበር ዋናው መንገድ መሆኑን፤
23. ሙስሊም የሆነ ሰው ከጂሃድ መስነፍ እንደሌለበት፤
24. ከአላህ ዲን እንቅፋት መሆንና በአላህ አናቅፅ መካድ በተከበረው ወር ከመዋጋት ወንጀሉ እንደሚበልጥ፤
25. ከሓዲያን በሙስሊሞች ላይ በሚከፍቱት ጦርነት የሚያልሙት ሙስሊሞችን ወደ ክህደት ለመመለስ መሆኑን፤
26. ከኢስላም ወደ ክህደት መመለስ የሰውን ልጅ ተግባር ከማጥፋትም አልፎ በገሀነም ውስጥ ዘወታሪ እንደሚያደርግ ;

وَأَتِمُّوا۟ ٱلْحَجَّ وَٱلْعُمْرَةَ لِلَّهِ ۚ فَإِنْ أُحْصِرْتُمْ فَمَا ٱسْتَيْسَرَ مِنَ ٱلْهَدْىِ ۖ وَلَا تَحْلِقُوا۟ رُءُوسَكُمْ حَتَّىٰ
يَبْلُغَ ٱلْهَدْىُ مَحِلَّهُۥ ۚ فَمَن كَانَ مِنكُم مَّرِيضًا أَوْ بِهِۦٓ أَذًى مِّن رَّأْسِهِۦ فَفِدْيَةٌ مِّن صِيَامٍ
أَوْ صَدَقَةٍ أَوْ نُسُكٍ ۚ فَإِذَآ أَمِنتُمْ فَمَن تَمَتَّعَ بِٱلْعُمْرَةِ إِلَى ٱلْحَجِّ فَمَا ٱسْتَيْسَرَ مِنَ ٱلْهَدْىِ ۚ فَمَن
لَّمْ يَجِدْ فَصِيَامُ ثَلَٰثَةِ أَيَّامٍ فِى ٱلْحَجِّ وَسَبْعَةٍ إِذَا رَجَعْتُمْ ۗ تِلْكَ عَشَرَةٌ كَامِلَةٌ ۗ ذَٰلِكَ لِمَن لَّمْ يَكُنْ
أَهْلُهُۥ حَاضِرِى ٱلْمَسْجِدِ ٱلْحَرَامِ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿١٩٦﴾
ٱلْحَجُّ أَشْهُرٌ مَّعْلُومَٰتٌ ۚ فَمَن فَرَضَ فِيهِنَّ ٱلْحَجَّ فَلَا رَفَثَ وَلَا فُسُوقَ وَلَا جِدَالَ فِى ٱلْحَجِّ ۗ وَمَا
تَفْعَلُوا۟ مِنْ خَيْرٍ يَعْلَمْهُ ٱللَّهُ ۗ وَتَزَوَّدُوا۟ فَإِنَّ خَيْرَ ٱلزَّادِ ٱلتَّقْوَىٰ ۚ وَٱتَّقُونِ يَٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿١٩٧﴾

**196-197.** ሐጅንና ዑምራን ለአላህ ብቻ ብላችሁ በትክክል ፈፅሙ። ከጀመራችሁ በኋላ ብትታገዱም ከመስዋእት የቻላችሁትን መሰዋት አለባችሁ። ምስዋእቱ ከመታረጃው ስፍራ እስኪደርስ ድረስ ራሶቻችሁን አትላጩ። ከናንተም ውስጥ በሐጅ ላይ ሁኖ የታመመ ወይም በራስ ቅሉ ላይ ጉዳት የደረሰበት ሰው ቢላጭ ከመፆም ወይም መስዋዕትን ቤዛ መስጠት አለበት። ፀጥታም ባገኛችሁ ጊዜ እስከ ሐጅ መፈፀሚያ ቀን ድረስ በዑምራ አስቀድሞ በመፈፀም የተገላገለ ሰው ከምስዋእቱ የተገራውን (የቻለዉን) መሰዋት አለበት። ያላገኘም ሰው ሶስት ቀናት በሐጅ ወራት ሰባትንም ቀናት ደግሞ በተመለሳችሁ ጊዜ መፆም አለበት። እነዚህ ሙሉ አስር (ቀናት) ናቸው። ይህም (ህግ) ቤተሰቦቹ ከቅዱስ መስጊድ አቅራቢያ ላልሆኑ ነው። አላህንም ፍሩ። ሐጅ የሚፈፀመው በተወሰነለት ወራት ነው። እናም በእነርሱ ውስጥ ሐጅን ለመስራት ግዴታ የገባ ሰው ሐጅ ክንውን ውስጥ እያለ ሴትን መገናኘት፤ በአላህ ላይ ማመጽና ክርክር አያደርግም። የምትሰሩትን በጎ ስራ ሁሉ አላህ ያውቀዋል። ሙስሊሞች ስንቅ ያዙ። ከስንቅም ሁሉ በላጩ አላህን መፍራት ነው። የአእምሮ ባለቤቶች ሆይ!እኔን ብቻ ፍሩኝ።

ከላሟ ምዕራፍ (196) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- አንድ ሰው ዛዕፋራን በተባለ እፅዋት ፀጉሩን ተለቅልቆና ካቦርቱን አድርጎ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጣ። በኡምራ ምንምን እንዳደርግ ታዘኛለህ አላቸው። ከቅፅበት በኋላ ይህች አንቀፅ ወረደች እና ጠያቂውን ጥሩት አሉ። ልብሱን እንዲ ያወልቅና እንዲታጠብ በሐጅ የሚፈፀመውን ሁሉ እንዲፈፅም አዘዙት። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ቲርሚዚ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከላሟ ምዕራፍ (197) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የየመን ሰዎች ወደ ሐጅ ሲሄዱ በአላህ ተወክለናል በማለት ስንቅ አይዙም ነበር። ይህንን ድርጊት ለማቃናት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ቡኻሪ፤ ዋሒዲ ና ሱዩጢ)

لَيۡسَ عَلَيۡكُمۡ جُنَاحٌ أَن تَبۡتَغُواْ فَضۡلٗا مِّن رَّبِّكُمۡۚ فَإِذَآ أَفَضۡتُم مِّنۡ عَرَفَٰتٖ فَٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ
عِندَ ٱلۡمَشۡعَرِ ٱلۡحَرَامِۖ وَٱذۡكُرُوهُ كَمَا هَدَىٰكُمۡ وَإِن كُنتُم مِّن قَبۡلِهِۦ لَمِنَ ٱلضَّآلِّينَ ١٩٨
ثُمَّ أَفِيضُواْ مِنۡ حَيۡثُ أَفَاضَ ٱلنَّاسُ وَٱسۡتَغۡفِرُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ١٩٩

**198-199.** በሐጅ ጊዜ (በንግድ ስራ) ከጌታችሁ ትርፍን በመፈለጋችሁ በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። ከአረፋት በተንቀሳቀሳችሁ ጊዜ መሽአረል ሀረም ዘንድ ስትደርሱ አላህን አውሱ። ወደ ቀናው የኢስላም መንገድ ስለመራችሁም ዘክሩት። ቀደም ሲል በእርግጥ ከተሳሳቾች ነበራችሁ። ከዚያ (ቁረይሾች ሆይ!) ሰዎች ከተንቀሳቀሱበት ስፍራ ተንቀሳቀሱ የአላህንም ምህረት ለምኑ። አላህ በእጅጉ መሀሪና አዛኝ ነውና።

ከላሚ ምዕራፍ (198) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በድንቁርና ዘመን የነበሩ ዑካዝ፤ ሚጀነህ ዙልመጃዝ የተሰኙ እውቅ ገበያዎች ነበሩ። እነርሱ ሙስሊሞች ለሐጅ በሄዱበት የንግድ ስራ ማከናወን ስለከበዳቸው ነብዩን ስለ ጉዳዩ ስለ ጠየቋቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ቡኻሪ፤ ሃኪም፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከምዕራፉ (199) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የአረብ ጎሳና ነገድ በአረፋ ሜዳ ላይ ሲገኙ ቁረይሾችና እነሱን የሚከተሉ የየስሪብ ነገዶች ግን የበላይነት ስለሚሰማቸው ከሌላው ወገን ተለይተው በሙዝደሊፋ ላይ ይሰባሰቡ ነበር። ይህ አንቀፅ ድርጊታቸውን በመቃወም ወረደ። (ሙስሊም፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

فَإِذَا قَضَيْتُم مَّنَٰسِكَكُمْ فَٱذْكُرُوا۟ ٱللَّهَ كَذِكْرِكُمْ ءَابَآءَكُمْ أَوْ أَشَدَّ ذِكْرًا ۗ
فَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا وَمَا لَهُۥ فِى ٱلْءَاخِرَةِ مِنْ خَلَٰقٍ ٢٠٠
وَمِنْهُم مَّن يَقُولُ رَبَّنَآ ءَاتِنَا فِى ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ حَسَنَةً وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ٢٠١
أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ نَصِيبٌ مِّمَّا كَسَبُوا۟ ۚ وَٱللَّهُ سَرِيعُ ٱلْحِسَابِ ٢٠٢

**200-202.** የሐጅ ስራዎቻችሁን በፈፀማችሁ ጊዜ አባቶቻችሁን እንደምታወሱ ወይም ከእሱ ይበልጥ የበረታን ማውሳት አላህን አውሱ። ከሰዎችም ውስጥ፡- ጌታችን ሆይ!በምድረ ዓለም መልካም እድልን ስጠን የሚል ሰው አለ። ለእርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ምንም ድርሻ የለውም። ከእነርሱ ውስጥ «ጌታችን ሆይ! በምድር ዓለም ደግን ነገር (ፀጋን) በመጨረሻይቱ ሀገርም ደግን ነገር (ገነትን) ስጠን። ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን» የሚሉ ሰዎች አሉ። እነዚያ ከሰሩት በጎ ስራ ለነርሱ ድርሻ አላቸው። አላህም ምርመራው ፈጣን ነው።

ከላሚ ምዕራፍ (200) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አረቦች በሐጅ ጊዜ በየመድረኩ የቅድመ አያቶቻቸውን ተግባርና ዝና በማውሳት እርስ በእርሳቸው ይፎካከሩ ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

۞ وَٱذْكُرُوا۟ ٱللَّهَ فِىٓ أَيَّامٍ مَّعْدُودَٰتٍ ۚ فَمَن تَعَجَّلَ فِى يَوْمَيْنِ فَلَآ إِثْمَ عَلَيْهِ وَمَن تَأَخَّرَ
فَلَآ إِثْمَ عَلَيْهِ ۚ لِمَنِ ٱتَّقَىٰ ۗ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّكُمْ إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ٢٠٣

**203.** በተወሰኑ ቀናት ውስጥ (በሚና ጠጠሮችን ስትወረውሩ) አላህን አውሱ። በሁለት ቀናት ውስጥ ለመሄድ የተቻኮለ ሰው በእርሱ ላይ ኃጢአት የለበትም። የቆየም ሰው ኃጢአት የለበትም። ይህ ምህረት አላህን ለፈራ ሰው ሁሉ ነው። አላህንም ፍሩ። እናንተ ወደ እርሱ የምትሰበሰቡ መሆናችሁንም እወቁ።

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُعۡجِبُكَ قَوۡلُهُۥ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَيُشۡهِدُ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا فِي قَلۡبِهِۦ وَهُوَ أَلَدُّ
ٱلۡخِصَامِ ﴿٢٠٤﴾ وَإِذَا تَوَلَّىٰ سَعَىٰ فِي ٱلۡأَرۡضِ لِيُفۡسِدَ فِيهَا وَيُهۡلِكَ ٱلۡحَرۡثَ وَٱلنَّسۡلَۚ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ
ٱلۡفَسَادَ ﴿٢٠٥﴾ وَإِذَا قِيلَ لَهُ ٱتَّقِ ٱللَّهَ أَخَذَتۡهُ ٱلۡعِزَّةُ بِٱلۡإِثۡمِۚ فَحَسۡبُهُۥ جَهَنَّمُۖ وَلَبِئۡسَ ٱلۡمِهَادُ ﴿٢٠٦﴾

**204-206.** ከሰዎችም ውስጥ እርሱ ክርክረ ብርቱ ሲሆን በቅርቢቱ ሕይወት ንግግሩ የሚያስደስትህ እና ግና ከጠላቶች ሁሉ እጅግ የከፋ፤ በልቡ ውስጥ በሚያጠነጥነው ነገር ላይ አላህን የሚያስመሰክር ሰው አለ። (ከአንተ) በዞረ ጊዜ በምድር ላይ በውስጧ ሊያበላሽና አዝመራንና እንሰሳዎችን ሊያጠፋ ይሮጣል። አላህም ጥፋትን አይወድም። ለእርሱ አላህን ፍራ በተባለ ጊዜ ትዕቢት (በኃጢአት ስራ ላይ) ይገፋፋዋል:- ገሀነምም ለእሱ በቂው ናት። እርሷም በእርግጥ የከፋች ምንጣፍ ናት።

ከላሚ ምዕራፍ ከ (204-205) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- አል አኽነስ ኢብኑ ሸሪቅ የተባለ ሰው ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ ኢስላምን መቀበሉንና እርሳቸውንም እንደሚወዳቸው ገለፀላቸው። ይህን በመሀላ ካረጋገጠ በኋላ ወደ ኋላ ዞሮ የሙስሊሞችን አዝርዕት አቃጥሎ አህዩቻቸውንም ገደለ። በቅፅበትም ወደ ሀገሩ ተመለሰ። ይህ አንቀፅ ይህንን ክስተት መሰረት አድርጎ ነው የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ ና ሱዩጢ)

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَشۡرِي نَفۡسَهُ ٱبۡتِغَآءَ مَرۡضَاتِ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ رَءُوفُۢ بِٱلۡعِبَادِ ﴿٢٠٧﴾

**207.** ከሰዎችም ውስጥ የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ሲል ነፍሱን የሚሸጥ ሰው አለ። አላህ ለባሮቹ በጣም ሩህሩህ ነው።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱدۡخُلُواْ فِي ٱلسِّلۡمِ كَآفَّةً وَلَا تَتَّبِعُواْ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوٌّ
مُّبِينٌ ﴿٢٠٨﴾ فَإِن زَلَلۡتُم مِّنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَتۡكُمُ ٱلۡبَيِّنَٰتُ فَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٢٠٩﴾

**208-209.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሆይ!) ሁላችሁም ለአላህ በመታዘዝ እጅ (ስጡ) ወደ አላህ መንገድ ጠቅልላችሁ ግቡ። የሰይጣንን እርምጃዎችን አትከተሉ:- እርሱም ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና። ግልፅ ማስረጃዎች ከመጡላችሁ በኋላ እውነትን ከመቀበል ብታፈገፍጉ አላህ አሸናፊና ጥበበኛ መሆኑን እወቁ።

ከላሚ ምዕራፍ (208) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ዐብዱላህ ኢብኑ ሰላም አንድ የአይሁድ ምሁራን ቡድን መጥቶ ለነብዩ (ﷺ) ተውራት የአላህ መፅሐፍ መሆኑ ታውቋል። ስለዚህ ሌሊት ሌሊት በእሱ ዒባዳ እንድናደርግ ፍቀዱልን ብለው ስለጠየቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

هَلۡ يَنظُرُونَ إِلَّآ أَن يَأۡتِيَهُمُ ٱللَّهُ فِي ظُلَلٖ مِّنَ ٱلۡغَمَامِ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ
وَقُضِيَ ٱلۡأَمۡرُۚ وَإِلَى ٱللَّهِ تُرۡجَعُ ٱلۡأُمُورُ ﴿٢١٠﴾

210. አላህና መላዕክቱ ከዳመና በሆኑ ጥላዎች ዉሥጥ ሆነው ወደ እነርሱ እንዲመጡና ጉዳዩ እንዲወሰን እንጂ ሌላ ምንን ይጠባበቃሉ?። ነገሮችም ሁሉ ወደ አላህ ይመለሳሉ።

سَلۡ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ كَمۡ ءَاتَيۡنَٰهُم مِّنۡ ءَايَةِۭ بَيِّنَةٖۗ
وَمَن يُبَدِّلۡ نِعۡمَةَ ٱللَّهِ مِنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَتۡهُ فَإِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ﴿٢١١﴾

211. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የኢስራኤል ልጆች አላህ ምን ያህል ግልፅ ተዐምር እንደሰጣቸው ጠይቃቸው። የአላህን ፀጋ ከመጣለት በኋላ የሚለውጥ ሰው ሁሉ የአላህ ቅጣት ብርቱ ነው።

زُيِّنَ لِلَّذِينَ كَفَرُواْ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَا وَيَسۡخَرُونَ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْۘ
وَٱلَّذِينَ ٱتَّقَوۡاْ فَوۡقَهُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۗ وَٱللَّهُ يَرۡزُقُ مَن يَشَآءُ بِغَيۡرِ حِسَابٖ ﴿٢١٢﴾

212. ለእነዚያ በአላህ ለካዱት ሰዎች ሁሉ። በአመኑት ሰዎች የሚሳለቁ ሲሆኑ ቅርቢቱ ሕይወት ተሸለመችላቸው። እነዚያ አላህን የሚፈሩ ሰዎች በትንሳኤ ቀን ከበላያቸው ናቸው። አላህ ለፈለገው ሰው ወደር የለሽ ገፀ በረከቱን ይሰጣልና።

كَانَ ٱلنَّاسُ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ فَبَعَثَ ٱللَّهُ ٱلنَّبِيِّـۧنَ مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ وَأَنزَلَ مَعَهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ
بِٱلۡحَقِّ لِيَحۡكُمَ بَيۡنَ ٱلنَّاسِ فِيمَا ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِۚ وَمَا ٱخۡتَلَفَ فِيهِ إِلَّا ٱلَّذِينَ أُوتُوهُ مِنۢ بَعۡدِ
مَا جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَٰتُ بَغۡيَۢا بَيۡنَهُمۡۖ فَهَدَى ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لِمَا ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ مِنَ ٱلۡحَقِّ
بِإِذۡنِهِۦۗ وَٱللَّهُ يَهۡدِي مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٍ ﴿٢١٣﴾

213. ሰዎች ሁሉ (አላህን አንድ በማድረግ) አንድ ሕዝብ ነበሩ። (ከዚያ ተለያዩ)። ከዚያ አላህ ነብያትን ለመልካም ሰዎች በጀነት አብሳሪዎችና ለመጥፎ ሰዎች ደግሞ ከእሳት አስጠንቃቂዎች አድርጎ ላከ። ከነሱ ጋርም ከሰዎቹ መካከል በዚያ እነርሱ በተለያዩበት ነገር ይፈርድ ዘንድ መጽሐፍትን በእውነት አወረደ። በእርሱ ግልፅ አስረጂዎች ከመጡላቸው በኋላ

በመካከላቸው በተፈጠረው ምቀኝነት ሰበብ እነዚያው መጽሐፍትን የተሰጡት ሰዎች እንጂ አልተለያዩበትም። አላህ እነዚያን በአላህ ያመኑትን ሰዎች በእነርሱ የተለያዩበትን እውነታ ይገነዘቡ ዘንድ በፈቃድ መራቸው። አላህ የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራዋል።

أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُوا۟ ٱلْجَنَّةَ وَلَمَّا يَأْتِكُم مَّثَلُ ٱلَّذِينَ خَلَوْا۟ مِن قَبْلِكُم ۖ مَّسَّتْهُمُ ٱلْبَأْسَآءُ وَٱلضَّرَّآءُ وَزُلْزِلُوا۟ حَتَّىٰ يَقُولَ ٱلرَّسُولُ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مَعَهُۥ مَتَىٰ نَصْرُ ٱللَّهِ ۗ أَلَآ إِنَّ نَصْرَ ٱللَّهِ قَرِيبٌ ﴿٢١٤﴾

**214.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በእውነቱ የእነዚያ ከበፊታችሁ ያለፉት ምዕመናንን ያጋጠመ መከራ የመሰለ ሳይመጣባችሁ ገነትን ልትገቡ ታስባላችሁን? መልዕክተኛውና እነዚያ ከእርሱ ጋር ያመኑት የአላህ እርዳታ መቼ ነው? እስከሚሉ ድረስ መከራና ጉዳት ደረሰባቸው። ተርበደበዱም አስተውሉ የአላህ እርዳታ በእርግጥ ቅርብ ነው ተባሉም።

يَسْـَٔلُونَكَ مَاذَا يُنفِقُونَ ۖ قُلْ مَآ أَنفَقْتُم مِّنْ خَيْرٍ فَلِلْوَٰلِدَيْنِ وَٱلْأَقْرَبِينَ وَٱلْيَتَـٰمَىٰ وَٱلْمَسَـٰكِينِ وَٱبْنِ ٱلسَّبِيلِ ۗ وَمَا تَفْعَلُوا۟ مِنْ خَيْرٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ﴿٢١٥﴾

**215.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምንን (ለማን) እንደሚለግሱ ይጠይቁሃል። «ከየትኛውም ሀብት የምትለግሱት ለወላጆች፣ ለቅርብ ዘመዶች፣ ለየቲሞች፣ ለድሆችና ለመንገደኞች ሊሆን ይገባል» ከበጎ ነገርም ማንኛውንም ብትሰሩ አላህ እርሱን አዋቂ ነው በላቸው።

ከላሟ ምዕራፍ (215) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዐምር ቢን ጀሙህ የተባለ ሙስሊም ባለሀብት ሰው ለነብዩ (ﷺ) ለማንና ምንን እንስጥ የሚል ጥያቄ ባቀረበበት ጊዜ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (196-215) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሐጅን ወይም ዑምራን ለማድረግ ኢህራም ያደረገ የመጀመሪያ የሐጅ ፀሎት እውን ማድረግ ግዴታው መሆኑን፤
2. ሐጅን ለማድረግ ኢህራም ቢያደርግም በተለያዩ ምክንያቶች ከሐጂ ስራው የተደናቀፈ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት፤
3. በኢህራም ወቅት የተከለከሉ ነገሮችን የሰራ ሰው ለማካካሻ ምን ማከናወን እንደሚገባው፤
4. ተመቱዕ የሐጅ ተጓዥ ምንምን መፈፀም እንደሚገባው፤

5. ሐጅና ዑምራ ግዴታ መሆናቸውን፤
6. የሐጅና የዑምራ ግዴታዎችና ሱናዎችን ማሟላት እንደሚገባ፤
7. የዑምራ ፀሎት ግዴታ ነው ለሚሉ ክፍሎች መረጃነት ማገልገሉ፤
8. የትርፍ ሐጅና ዑምራን ለመፈፀም የጀመሩ ሰዎች ከጀመሩት እስከመጨረሻው ድረስ መፈፀም ግዴታ መሆኑን፤
9. በሁለቱም ሆነ በአንዱ ኢህራም ያደረገ ከኢህራሙ ሊወጣ የሚችለው በአንቀፁ በተጠቀሰው መንገድ ብቻ እንደሆነ፤
10. ከሶስቱ የሐጅ ፀሎት ስርዓት አንዱ ተመቱዕ ሲሆን በዚህ የሀረመ ሰው ከአስረኛው ቀን በፊት መፈታት እንደማይችል፤
11. ከሶስቱ የሐጅ ዓይነቶች አንዱ ሐጅን ነጥሎ መስራት ሲሆን ይህንን የመረጠ ሰው እርድ እንደሌለበት፤
12. ከሐጅ አሰራር መንገዶች መካከል ተመቱዕን የመረጠ በሐጅ ወራችንም ቢሆን መፈፀም እንደሚችል፤
13. ከሐጅ ወራት በፊት ለሐጅ ኢህራም ማድረግ እንደማይቻል እንግራለን።
14. በሐጅ በኢህራም ውስጥ ሆኖ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ፤ አላስፈላጊ ቃላትና ስድቦችን መናገር የተከለከለ መሆኑን፤
15. መልካም ስራዎች በማንኛውም ጊዜ የተወደዱ ቢሆኑም በሐጅ ወቅት ግን በይበልጥ ተፈላጊ እንደሆኑና የሚገባው ምንዳ በብዙ እጥፍ አድጎ እንደሚሰጥ፤
16. ለሐጅ ጉዞ ያደረገ ሰው እግረ መንገዱን የንግድም ሆነ ሌላ ስራ ቢሰራ ከሸሪዓ የማይጋጭ እስከሆነ የማይከለከል መሆኑን፤
17. አላህን ለውለታዎቹ ማመስገን ለምንሰራቸው ኃጢአቶች ከርሱ ምህረት መለመን ተገቢ እንደሆነ፤
18. በአረፋ ጋራ ላይ መቆሙ ተገቢ እንደሆነ፤
19. በሙዝደሊፋ ላይ የአላህን ስም ማውሳት እንደሚገባ፤
20. የሙዝደሊፋ ተግባር ከአረፋ በኋላ ስለ መሆኑ፤
21. አረፋም ሆነ ሙዝደሊፋ የሐጅ ፀሎት ከሚፈፀምባቸው ቦታዎች መሆናቸውን፤
22. የአረፋ ጋራ ከሀረም ውጭ መሆኑንና የሙዝደሊፋ ደግሞ ከሀረም ክልል ውስጥ መሆንን፤
23. ሐጅ አድራጊዎች በሚና ቆይታቸው ወቅት የአላህን ታላቅነት፤ ብቸኝነት፤ ኃያልነት የሚያወሱ ዚክሮች፤ እየደጋሙ ማለታቸው ተገቢ መሆኑንና ሶስት ሌሊቶች በሚና ተራራ ላይ ማሳለፋቸው ተወዳጅ እንደሆነ ሆኖም ሶስት ሌሊቶችን ማሳለፍ ያልፈለገ በሁለተኛው ቀን መመለስ እንደሚችል፤
24. የማይቀረው የሞት ቀጠሮና ከዚያም በኋላ ያሉትን ክስተቶች (የመቃብር ህይወት፤ ቂያማ፤ ሂሳብ ማድረግ ሌሎችንም ማስታወሱ አላህን ለመፍራት እንደሚያነሳሳ፤
25. ኢህራም ማለት ለሐጅ ወይም ለዑምራ ስራ ቁርጠኛ ሀሳብ በማድረግ የሐጅ ስራ ከመጀመር ጊዜ አንስቶ እስከ መጨረሻዋ የሐጅ ስራ ድረስ የሚቆይበት ጊዜ ሲሆን በነዚህ የሐጅ ማከናወኛ ጊዜ ሐጅ አድራጊው ኢህራም ውስጥ ነው ያለው እንደሚሰኝ፤
26. አንደበተ ርዕቱነትና የማሳመን ችሎታ ከአላህ የሚሰጥና ሰው በራሱ ሀይሉና ችሎታ ሊያገኘው የማይችለው ነገር መሆኑን በማመን በአንደበተ ርዕቱነት ከመመካት መታቀብ ያስፈልጋል።

27. በሰዎች መሀከል ክፋት የተጠናወተው ማለት መጥፎ ነገሮችን ራሱ መስራቱ ሳይበቃው ሌሎችም እንዲሰሩት በማድረግ በምድር ላይ ጥፋት እንዲስፋፋ የሚያደርግ ነው።
28. «አላህን ፍራ» የሚል ምክር አዘል አስተያየት የጣሰው ማንኛው ሰው «አላህን ፍራ» ብሎ ለመከረው ወንድሙ የቁጣ ስሜት ማሳየት አይኖርበትም። እንዲሁም የአላህን ሃይማኖት (ኢስላም) ክብር ከፍ ለማድረግ በገንዘብ በጊዜና በሕይወት መስዋዕትነት መክፈልና መታገል፤ እንደሚገባ፤
29. የአላህን ሕግጋት በሙሉ ያለምንም ማመንታትና ማወላወል በሙሉ ልብ መቀበል ተገቢ ነው።
30. አላህ የከለከላቸውን ክልከላዎች በመተላለፍ ሀራምን (የተከለከለን) ሐላል እንደሆነ የሚናገር፤ ግዴታዎችን የሚያጣጥልና የሚተው የሰይጣን ተከታይ ነው።
31. ታላላቅ ወንጀሎችን መፈፀም አሰቃቂ ቅጣት የሚያስከትል እንደሆነ መገንዘብና እነዚህን ወንጀሎች ከመዳፈር በፊት የአላህን ቅጣት በማስታወስ ከወንጀሎች መታቀብ ያስፍልጋል። የትንሳኤ ዕለት አላህ ትክክለኛ ፍርድን ለሕዝቦች በሙሉ ይሰጣል። ብያኔው ፍትሃዊና ይግባኝ የለሽ ይሆናል። ኃጢአትን መስራቱ የታወቀው ሰው ነገ ከነገወዲያ ከኃጢአቴ ተመልሼ ንሰሃ እገባለሁ እያለ ንሰሀ መግቢያ ሰዓቱን ማራዘም የተከለከለ ነው። ተውበትን ዛሬውን በመግባት ኃጢአትን መተው ያስፈልጋል። ይህችን መሰል አንቀፅ የአላህ የምርጫ ባህሪያትን መቀጣጫ መውረድ፤ መምጣት የመሰሉ ባህሪያት ያረጋግጣል፤
32. አላህ ለፍጡራኑ የዋለላቸውን መጠነ ሰፊ ፀጋዎች መካድ አስከፊ የሆነ አደጋን የሚያስከትል እንደሆነ፤
33. በዚህች ዓለም ብልጭልጭ ኃላፊና ጠፊ በሆኑ ነገሮች በመታለል አኼራን መዘንጋት መጨረሻው አደጋ እንደሆነ፤
34. የኢስራኢል ልጆች ለዚያ ሁሉ ውድቀት የበቁት የአላህን ውለታ ባለማመስገናቸው መሆኑን፤
35. ተውሒድ (አላህን በአምልኮ አንድ ማድረግ) በተፈጥሮ ሰዎች የሚያውቁትና በሰዎች ዘንድ መሰረት ያለው ነገር ሲሆን ሽርክ (አምልኮን ከአላህ ውጭ ለሆነ አካል ማድረግ) ሰዎች ከጊዜ በኋላ ስሜታቸውን መከተልና ፍጡራንን በመፍራት አሊያም ለግል ጥቅማቸው ሲሉ የፈጠሩትን መጤ ነገር ማምለክ ነው። የእነዚህ ተልዕኮ ህዝቡን ከማስተማር በተጨማሪ ተልዕኮአቸውን (ተውሒድን) ተቀብሎ ያመነን በጀነት ማብሰርና የካደን ደግሞ በጀሀነም ቅጣት ማስጠንቀቅ ነበር። የአንድን ኡመት (ህዝብ) ክስረትና ውድቅት ከሚመመሰክሩ ድርጊቶች መካከል እናምንበታለን ብለው በሚሉት መፅሐፍ ላይ የተለያዩ አቋም መያዛቸው ዋነኛ ሆኖ ይገኛል። ሙስሊሞች ያልተበረዘውን ቁርአን ሐዲስ የህይወታቸው መመሪያ አድርው በመያዝ በቁርአን በሐዲስ ብቻ የሚመሩ መሆኑ ይገባቸዋል። ሂዲያን (ወደ ቀናው መንገድ መመራትን) የሚሰጠው አንድ አላህ ብቻ በመሆኑ ሂዳያን ከእርሱ ብቻ መለመን እንዳለብን፤
36. የአላህ ሕግጋት የሰው ልጅ ሰዎች ከሚፈተኑባቸው ነገሮች በመሆናቸው ህግጋትን በመጠበቅ ፈተናን ማለፍ እንደሚገባ፤
37. የደጋግ ሰዎችን መልካም አርአያ መከተል ግዴታ እንደሆነ፤
38. ነብያት የሰው ልጅ እንደመሆናቸው ተራ ሰዎች የሚያጋጥሟቸው ክስተቶች በሙሉ እነሱን ሊያግጥሟቸው እንደሚችሉና ነብዩ (ﷺ) እነዚህን የተለመዱ መልካምም ሆነ መጥፎ አጋጣሚዎች ማስተናገዳቸውን እንማራለን።

كُتِبَ عَلَيْكُمُ ٱلْقِتَالُ وَهُوَ كُرْهٌ لَّكُمْ ۖ وَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ
وَعَسَىٰٓ أَن تُحِبُّوا۟ شَيْـًٔا وَهُوَ شَرٌّ لَّكُمْ ۗ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ٢١٦

216. (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ከሓዲያንን መጋደል በእናንተ ዘንድ የሚወደድ ባይሆንም በእናንተ ላይ በግዴታነት ተደነገገ። አንድ ነገር ለእናንተ ጥሩ ቢሆንም ምንአልባት ትጠሉት ይሆናል። አንድንም ነገር እርሱ ለእናንተ መጥፎ ሆኖ እያለ ትወዱት ይሆናል። አላህ የሚሻላችሁን ያውቃል። እናንተ ግን አታውቁም።

يَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلشَّهْرِ ٱلْحَرَامِ قِتَالٍ فِيهِ ۖ قُلْ قِتَالٌ فِيهِ كَبِيرٌ ۖ وَصَدٌّ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ
وَكُفْرٌۢ بِهِۦ وَٱلْمَسْجِدِ ٱلْحَرَامِ وَإِخْرَاجُ أَهْلِهِۦ مِنْهُ أَكْبَرُ عِندَ ٱللَّهِ ۚ وَٱلْفِتْنَةُ أَكْبَرُ مِنَ
ٱلْقَتْلِ ۗ وَلَا يَزَالُونَ يُقَـٰتِلُونَكُمْ حَتَّىٰ يَرُدُّوكُمْ عَن دِينِكُمْ إِنِ ٱسْتَطَـٰعُوا۟ ۚ وَمَن يَرْتَدِدْ
مِنكُمْ عَن دِينِهِۦ فَيَمُتْ وَهُوَ كَافِرٌ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ حَبِطَتْ أَعْمَـٰلُهُمْ فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْـَٔاخِرَةِ ۖ
وَأُو۟لَـٰٓئِكَ أَصْحَـٰبُ ٱلنَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَـٰلِدُونَ ٢١٧

217. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በተከበረው ወር (በረጀብ) ስለመጋደል ይጠይቁሃል። በእነርሱ ውስጥ መጋደል ታላቅ ኃጢአት ነው። ግን ከአላህ መንገድ ሰዎችን መከልከል፤ በእርሱም መካድ ከተከበረው መስጊድ (ማገድ)፤ ባለቤቶቹንም ከእርሱ ማፈናቀል አላህ ዘንድ ይበልጥ ታላቅ ወንጀል ነው። ፈተናም (ማጋራትም) ከመግደል ይበልጥ ከባድ ነው። ከሓዲያን ቢችሉ ከሃይማኖታችሁ እስኪመልሷችሁ ድረስ የሚዋጓችሁ ከመሆን አይቦዝኑም። ከናንተ ውስጥ ከሀይማኖቱ የሚመለስና እርሱ ከሃዲ ሆኖ የሚሞት ሰው ሁሉ እነዚያ በጎ ስራቸው በቅርቢቱም ሀገር ሆነ በመጨረሻይቱ ሀገር ተበላሸች። እነዚህ ዓይነት ሕዝቦች የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱም በእርሷ ውስጥ ለዘላለም ይቆያሉ።

ከላሟ ምዕራፍ (217) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዐብደላህ ቢን ጀህሽ በተባለው ሶሃባ የሚመራው ጦር ዐምር ኢብኑ አልሀድረሚ የተባለውን አዋኪ ሰው በመንገድ ላይ አግኝቶ ይገድለዋል። ወሩ የረጀብ ወር የመጨረሻዋ ቀን ላይ መሆኗን አላወቁም ነበር። የቁረይሽ ከሓዲያን ይህን አጋጣሚ በመጠቀምን ሙሐመድ በተከበረው ወር እንኳን ሳይቀር ይዋጋል የሚል ትችት ስላቀረቡ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَٱلَّذِينَ هَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ
أُوْلَٰٓئِكَ يَرْجُونَ رَحْمَتَ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٢١٨﴾

**218.** እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑትና እነዚያም ከሀገራቸው የተሰደዱ፣ በአላህም መንገድ ላይም የተጋደሉ፣ እነዚያ የአላህን እዝነት ይከጅላሉ። አላህም እጅግ መሀሪና አዛኝ ነውና።

۞يَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلۡخَمۡرِ وَٱلۡمَيۡسِرِۖ قُلۡ فِيهِمَآ إِثۡمٞ كَبِيرٞ وَمَنَٰفِعُ لِلنَّاسِ
وَإِثۡمُهُمَآ أَكۡبَرُ مِن نَّفۡعِهِمَاۗ وَيَسۡـَٔلُونَكَ مَاذَا يُنفِقُونَۖ قُلِ ٱلۡعَفۡوَۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ
لَكُمُ ٱلۡأٓيَٰتِ لَعَلَّكُمۡ تَتَفَكَّرُونَ ﴿٢١٩﴾ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۗ وَيَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلۡيَتَٰمَىٰۖ
قُلۡ إِصۡلَاحٞ لَّهُمۡ خَيۡرٞۖ وَإِن تُخَالِطُوهُمۡ فَإِخۡوَٰنُكُمۡۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ ٱلۡمُفۡسِدَ مِنَ ٱلۡمُصۡلِحِۚ
وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَأَعۡنَتَكُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ﴿٢٢٠﴾

**219-220.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አዕምሮን ስለሚያሰክር መጠጥና ስለ ቁማር ይጠይቁሃል። በሁለቱም ታላቅ ኃጢአት አለባቸው። ምንም እንኳ ለሰዎች ጥቅም ቢኖራቸውም። ግን ኃጢአታቸው ከጥቅማቸው በጣም የገዘፈ ነው በላቸው። ምንን እንደሚመፀውቱም መጠኑን ይጠይቁሀል። የተረፉችሁን መፅውቱ በላቸው። እንደዚሁ ታስተውሉ ዘንድ አላህ ለእናንተ መልዕክቶቹን ይገልፅላችኋል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በቅርቢቱ ዓለም ሆነ በመጨረሻይቱ (ታስተነትኑ ዘንድ ይገልፅላችኋል)። መልክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ስለየቲሞችም ይጠይቁሀል የእነርሱን ሁኔታ ማሻሻል በላጭ ነው። የእነርሱ ጉዳይ ከናንተ ጋር ብትቀላቅሉም ወንድሞቻችሁ ናቸው። አላህም አጥፊውን ከአልሚው ለይቶ ያውቃል። አላህም በፈለገ ኖሮ ባስቸገራችሁ ነበር። አላህ ሁሉም ነገር አሸናፊና ጥበበኛ ነው በላቸው።

ከላሟ ምዕራፍ (219) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዑመር ኢብኑ አልኸጧብ የሚመሩት አንድ የሶሃቦች ቡድን ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ ስለኸምር (አስካሪ ነገር እና ስለ ቁማር) ንገረን ብለው በጠየቁት መሰረት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ቲርሚዚ፣ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከላሟ ምዕራፍ (220) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በአል. አንዓም (152) ኛው አንቀፅ ላይ ያለው የየቲሞችን ጉዳይ የሚያነሳው የቁርአን መልዕክት ወርዶ ሲነገራቸው የየቲሞችን ገንዘብ ከገንዘባቸው ለይተው ስላስቀመጡት ይህ አንቀፅ ወረደና ለጉዳት ታስቦ ካልሆነ በስተቀር ምንም ችግር የሌለው መሆኑን ገለፀ። (ሐኪም፣ ዋሒዲ፣ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَلَا تَنكِحُواْ ٱلۡمُشۡرِكَٰتِ حَتَّىٰ يُؤۡمِنَّۚ وَلَأَمَةٞ مُّؤۡمِنَةٌ خَيۡرٞ مِّن مُّشۡرِكَةٖ وَلَوۡ أَعۡجَبَتۡكُمۡۗ
وَلَا تُنكِحُواْ ٱلۡمُشۡرِكِينَ حَتَّىٰ يُؤۡمِنُواْۚ وَلَعَبۡدٞ مُّؤۡمِنٌ خَيۡرٞ مِّن مُّشۡرِكٖ وَلَوۡ أَعۡجَبَكُمۡۗ
أُوْلَٰٓئِكَ يَدۡعُونَ إِلَى ٱلنَّارِۖ وَٱللَّهُ يَدۡعُوٓاْ إِلَى ٱلۡجَنَّةِ وَٱلۡمَغۡفِرَةِ بِإِذۡنِهِۦۖ
وَيُبَيِّنُ ءَايَٰتِهِۦ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَتَذَكَّرُونَ ٢٢١

221. (ሙስሊሞች ሆይ!) በአላህ አጋሪ ሴቶችን በአላህ እስከሚያምኑ ድረስ አታግቧቸው። አጋሪይቱ ነፃ ሴት ምንም (በውበቷ) ብትደንቃችሁ እንኳ ያመነችው ባሪያ ሴት በእርግጥ ለእናንተ በላጭ ናት። ለአጋሪዎቹ እስከሚያምኑ ድረስ አትዳሩላቸው። ከአጋሪ ወንድ ምንም (በውበቱ) ቢደንቃችሁ እንኳ አማኝ ባሪያዎች ለእናንተ በላጭ ናቸው። እነዚያ አጋሪዎች ወደ እሳት ይጠራሉ። አላህ እነዚያን አጋሪዎች ወደ ገነትና ወደ ምህረት ይጠራል። ህግጋቱንም ለሰዎች ይገልፃል እነርሱም ሊገሰፁ ይከጀላልና።

ከላሟ ምዕራፍ (221) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ኢብኑ አቢመርሰድ የተባለ ሶሃብይ ኢናቅ የተባለች ሙሽሪክ ሴትን ለማግባት ስለጠየቀ ነው ለእሱና መሰሎቹ ለመምከር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَيَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلۡمَحِيضِۖ قُلۡ هُوَ أَذٗى فَٱعۡتَزِلُواْ ٱلنِّسَآءَ فِي ٱلۡمَحِيضِ وَلَا تَقۡرَبُوهُنَّ حَتَّىٰ يَطۡهُرۡنَۖ
فَإِذَا تَطَهَّرۡنَ فَأۡتُوهُنَّ مِنۡ حَيۡثُ أَمَرَكُمُ ٱللَّهُۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلتَّوَّٰبِينَ وَيُحِبُّ ٱلۡمُتَطَهِّرِينَ ٢٢٢

222. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስለ ሴቶች የወር አበባ ይጠይቁሃል። እርሱ ጎጂ ነው በላቸው። እናም ሚስቶቻችሁን በወር አበባቸው ጊዜ ንፁህ እስከሚሆኑ ድረስ ለግንኙነት በፍፁም አትቅረቧቸው። ንፁህ በሆኑ ጊዜም ግን አላህ ባዘዛችሁ ቦታ ተገናኟቸው። አላህ ከኃጢአት ተመላሾችን ሁሉ ይወዳል። ንፅህናን የሚጠብቁትንም እንዲሁ ይወዳል በላቸው።

ከላሟ ምዕራፍ (222) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተፍሲር ምሁራን ዐረቦች በጃህሊያ ዘመን ሴቶች የወር አበባ ሲመጣባቸው ልክ እንደ መጁሳወች አብረዋቸው አይበሉም አይጠጡም፤ አይቀመጡም። ከዚያም አቡደርዳህ የተባለ ሶሃባ ወደ ነብዩ መጥቶ ሴቶች የወር አበባ ሲመጣባቸው ምን እናድርግ በማለት ሲጠይቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ኢብኑ ከሲር)

نِسَآؤُكُمۡ حَرۡثٞ لَّكُمۡ فَأۡتُواْ حَرۡثَكُمۡ أَنَّىٰ شِئۡتُمۡۖ وَقَدِّمُواْ لِأَنفُسِكُمۡۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱعۡلَمُوٓاْ
أَنَّكُم مُّلَٰقُوهُۗ وَبَشِّرِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٢٢٣ وَلَا تَجۡعَلُواْ ٱللَّهَ عُرۡضَةٗ لِّأَيۡمَٰنِكُمۡ أَن تَبَرُّواْ وَتَتَّقُواْ
وَتُصۡلِحُواْ بَيۡنَ ٱلنَّاسِۚ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ٢٢٤ لَّا يُؤَاخِذُكُمُ ٱللَّهُ بِٱللَّغۡوِ فِيٓ أَيۡمَٰنِكُمۡ
وَلَٰكِن يُؤَاخِذُكُم بِمَا كَسَبَتۡ قُلُوبُكُمۡۗ وَٱللَّهُ غَفُورٌ حَلِيمٞ ٢٢٥

**223-225.** ሚስቶቻችሁ ለእናንተ እርሻ ናቸው። እናም እርሻዎቻችሁን በፈለጋችሁት ሁኔታ ግንኙነት ፈፅሙ። ለነፍሶቻችሁ መልካም ስራን አስቀድሙ። አላህን ፍሩ። እናንተም ከእርሱ ጋር የምትገናኙ መሆናችሁን እውቁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምዕመናንንም በገነት አብስራቸው። (ሙስሊሞች ሆይ!) በአላህ ስም የፈፀማችሁት መሀላ በጎ ከመዋል አላህን ከመፍራትም ወይም በሰዎች መካከል እርቀ ሰላም ከማውረድ ሊያቅባችሁ አይገባም። አላህ (ለሚባለው ሁሉ) ሰሚ (ለሚፈጸመው ሁሉ ነገርም) አዋቂ ነው። ያለ አስተውሎት በምትፈፅሙት መሐላዎቻችሁ አላህ አይቀጣችሁም። ግን ልቦቻችሁ በፅኑ ባሰቡበት መሐላዎቻችሁ ይይዛችኋል። አላህ በጣም መሀሪ፤ ታጋሽ ነውና።

ከላሚ ምዕራፍ (223) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁዶች ሚስት በደረት ላይ ተኝታ በተለመደው የግንኙነት ቦታ ላይ የግብረስጋ ግንኙነት ከተፈፀመ የሚወለደው ልጅ አይኑ ሸውራራ ሆኖ ይወለዳል ብለው ያምኑ ነበር። ይህ አባባል ሀሰት መሆኑን ለመግለፅ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሙስሊም፤ ኢብኑ አልጀውዚ እና ዋሒዲ)

ከላሚ ምዕራፍ (224) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዐብዱላህ ኢብኑ ረዋሀ የተባለ ሶሃቢ የእህቱን ባል (አማቹን) በሽር ኢብኑል ኑማንን ላለማነጋገርና ከሚስቱም ጋር ላለማስታረቅ ምሎ ስለነበር ይህን ማድረግ እንደሌለበት ለመከልከል ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ዛዱል መሲር)

**ከላሚ ምዕራፍ (216-224) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መስፈርቱ የተሟላ ግዴታነት፤
2. በተከበሩት ወራት መጋደል የማይቻል እንደሆነ፤
3. ከሓዲያን ሙስሊሞችን ከመፈተን እንደማያርፉ፤
4. ለዲኑ ብለው የተሰደዱ ሁሉ በአላህ ዘንድ ያላቸው ማዕረግ፤
5. ስለ አስካሪ ነገር ቁማር ለቀረቡ ጥያቄዎች መልስ፤
6. ከየቲሞች ጋር ሊኖረን የሚገባን ግንኙነት፤
7. በአላህ የሚያጋሩ ሴቶችን ከማግባት ማስጠንቀቅ፤፤
8. የወር አበባን ህግን፤
9. ነብዩ ኢብራሂም ከጌታቸው የጠየቁትን ተዐምር፤
10. በአላህ መንገድ ላይ የሚከፈል. የገንዘብ ምፅዋቶች ክፍያቸው፤
11. በአላህ መንገድ ላይ እንሰጣለን የሚሉ ሰዎች መጠበቅ ያለባቸው ስርዓቶች፤
12. በአንደበት መለስለስ ምን ያህል ጥቅም እንዳለው፤
13. ለአላህ ብለው ገንዘባቸውን የሚያወጡ ሰዎች ምንዳቸው ከፍተኛ ስለመሆኑ፤
14. ገንዘባቸውን አብልተው ምንም ጥቅም የሌላቸውን መጠቆም፤
15. በዘካም ሆነ በሌላው ከመልካም ገንዘብ መስጠት እንዳለብን፤
16. አላህ ጥበብን ለፈለገው እንደሚሰጥ፤
17. ጂሃድ በሙስሊሞች ላይ ግድታ የሆነው ከኢስላምና ከሙስሊሞች ጠላትን ተንኮል ለመግታት መሆኑን፤

18. በተከበሩት ወሮች ጦርነት ስለ ማካሄድ ሶሃቦች ነብዩን (ﷺ) ስለመጠየቃቸው፤
19. ጣኦት አምላኪዎች አማኞችን ከትክክለኛ እምነታቸው እስከሚያስቀይሯቸው ድረስ ከመፈተን ወደ ኋላ እንደማይሉ፤
20. ለኢስላም ብለው ከተሰደዱ አላህ ዘንድ ያላቸው ማዕረግ፤
21. ሶሃቦች ስለ አስካሪ ነገር፤ ስለ ቁማር ጨዋታ ከገንዘባቸው ለድሆች ምን ያህሉን መስጠት እንዳለባቸው ነብዩን (ﷺ) ጠይቀው እንደነበር፤
22. የሰው ልጅ የታወቀ ደረጃው በጣም ውስን በመሆኑ የክስተቶችን የመጀመሪያ ሂደት በመመልከት ለማዘንም ሆነ ለመደሰት ቢቸኩሉም ነገሩ የተገላቢጦሽ ሆኖ በመጨረሻውም የድርጊቱ ፍፃሜና ውጤት ከመጀመሪያው ሂደት በተቃራኒው ሊሆን እንደሚችል በመገንዘብ የነገሮችን ሂደት በትዕግስትና በተስፋ እንደአመጣጡ ማስተናገድ እንደሚገባው፤
23. አላህ እንድንፈፅማቸው ያዘዘን ነገሮች ለምድራዊም ሆነ ለአኼራዊ ህይወታችን ደስታን የሚጎናፀፉ ተድላን የሚያስጨብጡ ጤናማ ሕይወት እንዲኖረን የሚያስችሉ እንደሆኑና በአንፃሩም እንዳንቀርባቸው እገዳ የተጣለባቸው ነገሮች ክስረትን፤ ጥፋትን ውድቀትን፤ ቅጣትን የሚያስከትሉ መጥፎ ነገሮች እንደሆኑ፤
24. አላህ በተለያዩ ነገሮች ማዕረግንና ክብርን ሰጥቷል። የመስጠት ብቸኛ ባለቤት በመሆኑ ከወራት መርጦ ለተወሰኑ ወራት ክብር እንደሰጠው። ሁሉ ከቦታዎች ደግሞ ካዕባን የተከበረ የእርሱ ቤት አድርጎታል።
25. ለአላህ ሃይማኖት ለኢስላም ሲባል ስደትን የሕይወት መስዋዕት መክፈልን ተገቢ ነው።
26. በኢስላም እምነቱን የቀየረ ሰው በፊት የሰራው ሁሉ እንደሚበላሽበትና ለጀሀነም የሚዳርገው ሲሆን የከፈረ ሰው ወደ ኢስላም ሲመለስ ደግሞ እንደገና ከዚያ በፊት ከሰራው መመለስና በአዲስ መስራት ይኖርበታል። ሰዎችን ከአላህ ዲን መከልከልና በአላህ አናቅፆች ማስተባባል ወንጀሉ በተከበሩት ወራት ከመዋጋት የበለጠ ይሆናል። ከሓዲያን ለሙስሊሞች ከልብ የመነጨ መራራ ጥላቻ አላቸው። ጂሃድ በሰዎች ዘንድ ከባድና የተጠላ ቢሆንም ብቸኛው የድል መንገድ ነው። የኢስላም ጠላቶች ሙስሊሞችን የሚዋጉበት ዋና ዓላማቸው በየትኛውም ዘዴ ወደ ክህደት ለመጥራት መሆኑን ከአናቅጹ እንማራለን።

لِّلَّذِينَ يُؤْلُونَ مِن نِّسَآئِهِمْ تَرَبُّصُ أَرْبَعَةِ أَشْهُرٍ ۖ فَإِن فَآءُو فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٢٢٦﴾
وَإِنْ عَزَمُوا۟ ٱلطَّلَٰقَ فَإِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٢٢٧﴾

**226-227.** እነዚያ ሚስቶቻቸውን ላለመገናኘት የሚምሉ ወንዶች ሁሉ አራት ወራት መጠበቅ አለባቸው። እናም መሀላቸውን ቢያጥፉም አላህ መሀሪ፤ አዛኝ ነው። ፍችን ለመፈፀም ፅኑ ውሳኔ ላይ ከደረሱ ደግሞ (ይፍቱ) አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ሁሉ ነገርም አዋቂ ነው።

ከላሟ ምዕራፍ (226) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በጃሂሊያ ዘመን በባልና በሚስት መካከል ይደረግ የነበረ መሀላ አመትም ሁለት ዓመትም ከዚያም የረዘመ ስለ ነበር አላህ ባል በአራት ወር ጊዜ ውስጥ ውሳኔውን እንዲወስን ይህን አንቀፅ አወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَٱلۡمُطَلَّقَٰتُ يَتَرَبَّصۡنَ بِأَنفُسِهِنَّ ثَلَٰثَةَ قُرُوٓءٖۚ وَلَا يَحِلُّ لَهُنَّ أَن يَكۡتُمۡنَ مَا خَلَقَ ٱللَّهُ فِيٓ أَرۡحَامِهِنَّ إِن كُنَّ يُؤۡمِنَّ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ وَبُعُولَتُهُنَّ أَحَقُّ بِرَدِّهِنَّ فِي ذَٰلِكَ إِنۡ أَرَادُوٓاْ إِصۡلَٰحٗاۚ وَلَهُنَّ مِثۡلُ ٱلَّذِي عَلَيۡهِنَّ بِٱلۡمَعۡرُوفِۚ وَلِلرِّجَالِ عَلَيۡهِنَّ دَرَجَةٞۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٢٢٨﴾

228. የተፈቱ ሴቶች (በራሳቸው ሕሊናዊ ሀላፊነት) ሶስትን ቁርእ (የወር አበባ) ይጠብቁ። እርቅን ከፈለጉ፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑ ከሆኑ አላህ በማህፀኖቻቸው ውስጥ የፈጠረውን ፅንስ ሊደብቁ አይፈቅድላቸውም። ባሎቻቸውም በእነዚህ ወራት ውስጥ የመመለስ መብታቸው ቅድሚያ ነው። ለሴቶች ግዳጅ እንዳለባቸው ሁሉ ፍትሀዊ መብትም አላቸው። ይሁንና ወንዶችም (የበለጠ ሀላፊነትን ስለሚሸከሙ) ብልጫ አላቸው ተጥሎባቸዋል። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

ٱلطَّلَٰقُ مَرَّتَانِۖ فَإِمۡسَاكُۢ بِمَعۡرُوفٍ أَوۡ تَسۡرِيحُۢ بِإِحۡسَٰنٖۗ وَلَا يَحِلُّ لَكُمۡ أَن تَأۡخُذُواْ مِمَّآ ءَاتَيۡتُمُوهُنَّ شَيۡـًٔا إِلَّآ أَن يَخَافَآ أَلَّا يُقِيمَا حُدُودَ ٱللَّهِۖ فَإِنۡ خِفۡتُمۡ أَلَّا يُقِيمَا حُدُودَ ٱللَّهِ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِمَا فِيمَا ٱفۡتَدَتۡ بِهِۦۗ تِلۡكَ حُدُودُ ٱللَّهِ فَلَا تَعۡتَدُوهَاۚ وَمَن يَتَعَدَّ حُدُودَ ٱللَّهِ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٢٢٩﴾

229. የመመለስ እድል የሚሰጠው ፍቺ ሁለት ጊዜ ብቻ ነው። ከዚህም በኋላ በመልካም መያዝ ወይም በበጎ አኳኋን ማሰናበት ነው። (ባሎች ሆይ!) የአላህን ህግጋት ያለማክበር ባል እና ሚስቱ ስጋት ካልኖረባቸው በስተቀር ከሰጣችኋቸው ነገር ምንንም ልትወስዱ ለእናንተ አይፈቀድላችሁም። የአላህን ሕግጋት አለመጠበቃቸውን ብትገነዘቡ በርሱ ነፃ ለማውጣት በምትፈጽመው ነገር* በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም። እኒህ የአላህ ሕግጋት ናቸው። አትተላለፏቸው። እነዚያ እነርሱ የአላህን ሕግጋት የሚተላለፉ ሁሉ እነዚያ እነርሱ (በደለኞች) አጥፊዎች ናቸው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐብባስ እንዳስተላለፉት የአነስ ብኑ ቀይስ ሚስት ወደ አላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ዘንድ መጥታ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በአነስ ኢብኑ ቀይስ ሥነ ምግባርና ሃይማኖት ላይ ስሞታ አላቀርብበትም። ነገር ግን እንደ ሙስሊምነቴ በኢስላም ላይ ክህደትን እጠላለሁ» አለቻቸው። የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ)፦ «በጥሎሽ መልክ የሰጠሽን የአትክልት ቦታ ትመልሺለታለሽን?» አሏት። እሷም «አዎን» አለች። የአላህ መልዕክተኛ ለሳቢት ኢብኑ ቀይስ «ሳቢት ሆይ! የአትክልት ቦታህን ውሰድና አንድ ጊዜ ፍታ» አሉት።

ከላሟ ምዕራፍ (229) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በጃሂሊያ ዘመን ወንድ ሚስቱን ፈትቶ፤ ኢዳዋ ከማለቁ በፊት የመመለስ መብቱ ሺህ ጊዜ እንኳን ቢፈታት የተጠበቀለት ነበር። በመሆኑም አንድ ግለሰብ ሚስቱን ፈትቶ ኢዳዋ ሲያልቅ ይመልሳታል «ወላሂ ወደ እኔ አላመጣሽም እስከመጨረሻውም ድረስ ነፃ አትሆኚም» አጣብቂኝ ውስጥ ከተታት ይህን ጊዜ ቢፈቷቸው እንኳን የተወገዘ እና የማይፈቀድ መሆኑን ለማስተማር ይህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ፤ ኢብኑ ከሲር እና ዋሒዲ)

فَإِن طَلَّقَهَا فَلَا تَحِلُّ لَهُۥ مِنۢ بَعۡدُ حَتَّىٰ تَنكِحَ زَوۡجًا غَيۡرَهُۥۗ فَإِن طَلَّقَهَا فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِمَآ
أَن يَتَرَاجَعَآ إِن ظَنَّآ أَن يُقِيمَا حُدُودَ ٱللَّهِۗ وَتِلۡكَ حُدُودُ ٱللَّهِ يُبَيِّنُهَا لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٢٣٠
وَإِذَا طَلَّقۡتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَبَلَغۡنَ أَجَلَهُنَّ فَأَمۡسِكُوهُنَّ بِمَعۡرُوفٍ أَوۡ سَرِّحُوهُنَّ بِمَعۡرُوفٖۚ
وَلَا تُمۡسِكُوهُنَّ ضِرَارٗا لِّتَعۡتَدُواْۚ وَمَن يَفۡعَلۡ ذَٰلِكَ فَقَدۡ ظَلَمَ نَفۡسَهُۥۚ وَلَا تَتَّخِذُوٓاْ ءَايَٰتِ
ٱللَّهِ هُزُوٗاۚ وَٱذۡكُرُواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡ وَمَآ أَنزَلَ عَلَيۡكُم مِّنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡحِكۡمَةِ
يَعِظُكُم بِهِۦۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ ٢٣١

**230-231.** ለሶስተኛ ጊዜ ከፈታት በኋላ ሌላን ባል እስካላገባችና እስካልተፈታች ድረስ ለእርሱ አትፈቀድለትም። ሁለተኛው ባል ከፈታት የአላህን ሕግጋት እንደሚጠብቁ ተስፋ ካደረጉ በመማለስ በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም። እነኘህ የአላህ ሕግጋት ናቸው። ለሚያውቁ ሕዝቦች ሁሉ ያብራራላቸዋል። (ሙስሊሞች ሆይ!) ሴቶቻችሁን በፈታችሁ እና የኢዳ ጊዜያቸውን ለማገባደድ በቀረቡ ጊዜ በመልካም መልሷቸው። ወይም በመልካም ሁኔታ ያለ አንድ ጉዳት አሰናብቷቸው። ለመጉዳትም ወሰን ታልፉባቸው ዘንድ አትያዟቸው። ይህን የሚሰራ ሰው ሁሉ ነፍሱን በእርግጥ በደለ። የአላህን አንቀፆች ማላገጫ አድርጋችሁ አትያዙ። የአላህን ፀጋ በእናንተ ላይ ያደረገውን ከመፅሐፍና (ከቁርአን) ከጥበብም (ከእሱና) በእርሱ የሚገስፃችሁ ሲሆን በእናንተ ላይ ያወረደውን አስታውሱ። አላህን ፍሩ። አላህ በሁሉ ነገር ላይ ሙሉ እውቀት ያለው መሆኑን እወቁ።

وَإِذَا طَلَّقۡتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَبَلَغۡنَ أَجَلَهُنَّ فَلَا تَعۡضُلُوهُنَّ أَن يَنكِحۡنَ أَزۡوَٰجَهُنَّ إِذَا تَرَٰضَوۡاْ
بَيۡنَهُم بِٱلۡمَعۡرُوفِۗ ذَٰلِكَ يُوعَظُ بِهِۦ مَن كَانَ مِنكُمۡ يُؤۡمِنُ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۗ ذَٰلِكُمۡ
أَزۡكَىٰ لَكُمۡ وَأَطۡهَرُۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ وَأَنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ٢٣٢

232. ሴቶቻችሁን (ከሶስት ጊዜ ባነሰ) በፈታችሁ እና የኢዳ ጊዜያቸውን በጨረሱ ጊዜ ጥንዶቹ በመካከላቸው ሕጋዊና ፍትሀዊ የጋራ ስምምነት ላይ ከደረሱ የቀድሞ ባሎቻቸውን ከማግባት አታስተጓጉሏቸው። ይህ ህግ ከናንተ መካከል በአላህና በመጨረሻ ቀን የሚያምን ሰው ሁሉ ይገሰፅበታል። ይህ ለእናንተ በላጭ ነው። አላህ የሚጠቅማችሁን ሁሉ ያውቃል። እናንተ ግን አታውቁም።

ከላሟ ምዕራፍ (232) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- መዕቂል ኢብኑ የሳር የተባለ ሶሃባ የአንድን ሌላ ሶሃባ እህት ለጋብቻ ጠይቆ ከዳረለት በኋላ ተጋብተው መኖር ይጀምራሉ። የኋላ ኋላ ሚስቱን በአንድ ፈታትና ሳይመልሳት ኢዳዋ አለፈ። በኋላ ባልና ሚስት ደግሞ ለመመለስ ፈለጉ። በዚህን ወቅት በድጋሚ ሙልቂብ ለወንደሟ ጥያቄውን ሲያቀርብ ወንድሟም በክብር ሰጠንህ ፈትተህታልና ደግሞ ልታገባት አትችልም ብሎ መለሰው። ሁኔታው አግባብ እንዳልሆነ ለማሳወቅ አላህ እነዚህን አናቅፅ አወረደ። ከዚያም ይኸው የሚስቱ ወንድም ለጌታዬ ታዛዥ ነኝ በማለት ሙልቂኢብኑ ጠርቶ ሰጠው። (ጦበሪ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

۞ وَٱلۡوَٰلِدَٰتُ يُرۡضِعۡنَ أَوۡلَٰدَهُنَّ حَوۡلَيۡنِ كَامِلَيۡنِۖ لِمَنۡ أَرَادَ أَن يُتِمَّ ٱلرَّضَاعَةَۚ وَعَلَى ٱلۡمَوۡلُودِ لَهُۥ رِزۡقُهُنَّ وَكِسۡوَتُهُنَّ بِٱلۡمَعۡرُوفِۚ لَا تُكَلَّفُ نَفۡسٌ إِلَّا وُسۡعَهَاۚ لَا تُضَآرَّ وَٰلِدَةُۢ بِوَلَدِهَا وَلَا مَوۡلُودٞ لَّهُۥ بِوَلَدِهِۦۚ وَعَلَى ٱلۡوَارِثِ مِثۡلُ ذَٰلِكَۗ فَإِنۡ أَرَادَا فِصَالًا عَن تَرَاضٖ مِّنۡهُمَا وَتَشَاوُرٖ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِمَاۗ وَإِنۡ أَرَدتُّمۡ أَن تَسۡتَرۡضِعُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُمۡ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡكُمۡ إِذَا سَلَّمۡتُم مَّآ ءَاتَيۡتُم بِٱلۡمَعۡرُوفِۗ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ٢٣٣

233. እናቶች ልጆቻቸውን ሁለት ሙሉ ዓመታትን ያጥቡ። ይህም ማጥባትን የተሟላ ለማድረግ በችሎታው ልክ ለሻ (ለፈለገ) ሰው ነው። በአባት ላይ ምግባቸውንና ልብሳቸውን የማቅረብ ግዴታ አለበት። ማንም ነፍስ ከችሎታዋ በላይ አትገደድምና። እናት በልጇ ምክኒያት ጉዳት እንዲደርስባት አይደረግም። አባትም በልጁ ምክንያት እንዲንገላታ መሆን የለበትም። በወራሽም ላይ የዚሁ ተመሳሳይ ሀላፊነት አለበት። ወላጆቹ በመልካም ፈቃድ ልጁን ከጡት መነጠል (ማስጣል) ቢፈልጉ በሁለቱም በሆነ መዋደድና መመካከር በሁለቱም ላይ ኃጢአት የለባቸውም። ለልጆቻችሁ ሌሎችን አጥቢዎችን ማስጠባት ብትፈልጉ የሰጣችሁትን ክፍያ በአግባቡ እስከሰጣችሁ ድረስ በማስጠባታችሁ በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። አላህን ፍሩ። አላህ የምትሰሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች መሆኑን እወቁ።

**ከላሟ ምዕራፍ አንቀፅ (221-233) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከአላህ በተወረዱ መፅሐፍት የማታምን ጣኦት አምላኪ ሴትን ማግባት በኢስላም የተከለከለ መሆኑን፤
2. ሙስሊም ሴቶችን በመፅሐፍ የሚያምንም ቢሆን ማግባት የማይፈቀድ መሆኑን፤
3. በመፅሐፍ የምታምን ሴት ለሚወለዱት ልጆች እስካላሰጋች ሙስሊም ወንድ ሊያገባት እንደሚፈቀድ፤
4. በሀላል ምክንያት ተገቢ ያልሆነ ስራን ማቋረጥ ተገቢ አለመሆኑን፤
5. አንድን ነገር ላለመስራት ከማለና መስራት አስፈለጊ መሆኑን ካመነበት ተግባሩን ፈፅሞ መቀጫውን መክፈል እንደሚችል፤
6. በግድ ያለ ፍላጎት የተገባ መሀላ እንደማያስጠይቅና አስቦና አቅዶ የሚፈፀም መሀላ ግን እንደሚያስጠይቅ፤
7. ከሴት ልጅ ጋር በወር አበባ ጊዜ የወሲብ ግንኙነት መፈፀም ክልክል መሆኑን፤
8. ሚስቱን ላለመገናኘት መሀላ የገባ ሰው የማካካሻ ቅጣት በመፈፀም የግብረስጋ ግንኙነት ማድረግ እንደሚችል፤
9. ሚስቱን ላለመገናኘት መሀላ የገባ ሰው በአራት ወራት ውስጥ ወደ እሷ ካልተመለሰ ሚስቱ ፍች እንደምትሆን፤
10. በምግብና በሌሎች ጉዳዮች ላይ ሙሽሪክንም ሆነ የቢድአ ሰዎችን መደባለቅ ከአቅም በላይ ካልሆነ ተገቢ እንዳልሆነ፤
11. ሴቶች ከወር አበባ ሲፀዱ ሙሉ አካላቸውን መታጠብ ተገቢ መሆኑን፤
12. ፅዳት በኢስላም በማንኛውም ጊዜና ቦታ ተገቢ እንደሆነ፤
    ሴት ልጅ ከወር አበባዋ እከምትፀዳ ድረስ ከግንኙነት መቆጠብ ግዴታዋ እንደሆነ፤
13. ከወር አበባዋ ስትፀዳ በውሃ ከታጠበች በኋላ ግንኙነት መፈቀዱን፤
14. ሴት ልጅ በአፍጋራዋ (በመቀመጫዋ) በኩል ግንኙነት ማድረግ መከልከሉን፤
15. በልጅ ማስረገገዋ አካል እስከሆነ ድረስ በየትኛውም ግንኙነት አይነት መጠቀም እንደሚቻል፤
16. በየትኛውም ሰዓትና ጊዜ አጋጣሚ የአላህን ህግ በመጠቀም ማስጠንቀቅ፤
17. የሰው ልጅ ጥቅሞች ሲደራረቡበት በጣም አስፈላጊውን ማስቀደም እንዳለበት፤
18. የሰው ልጅ አላህ በተግባር ጊዜ እንደሚፈልግ ሁሉ በንግግር ጊዜ እንዲሁ እንደሚፈልግ፤
19. በኢስላም ባልና ሚስት ቢያንስ በአራት ወር አንድ ጊዜ እንኳን የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ግዴታ እንደሆነ፤
20. ኸይር ነገርን ላለመስራት መማል ክልክል መሆኑ፤
21. ከባሏ ጋር የተፋታች ፅንስ ካለ መኖሩን መደበቅ እንደሌለበት፤ እንዲሁም የወር አበባ እንደመጣባት መደበቅ የለባትም፤
22. ከባሏ ጋር በአንድ ወይም በሁለት ዙር የተፈታች ሴት የኢዳ ጊዜዋ እስካልደረሰ ድረስ ባሏ ሊመልሳት መብት እንዳለው፤
23. ባል በሚስቱ ላይ ያለው መብት እንዲሁም ሚስትም በባሏ ላይ ያሏት መብቶች በዝርዝር ምን ምን እንደሆኑ፤
24. ወንድ ባለው ጥንካሬ መከራን የመቋቋም ብቃት ስላለው በጋብቻ ሕይወት ላይ የቤተሰቡና የሚስቱ ኃላፊ መሆኑን፤

25. ሴት ራሷን በተመለከተ በእርግዝናን፤ በወር አበባ እና በመሳሰሉት በምትናገረው እሷን ብቻ መቀበል እንደሚገባ፤
26. ሴትና ወንድ በመብት እኩል መሆናቸውና ወንድ ኃላፊነት እንዳለበት፤
27. ሴት በወንድ ላይ ያላት መብት እንደየገሀሩና እንደቦታ ብሎም እንደ ሰውየው አቅምና እንደ ዘመኑ እንደሚለዋወጥ፤
28. ሚስትን በማስቸገር ገንዘብ ከፍሎ እንድትፈታ ማድረግ ክልክል መሆኑ፤
29. በአንድ ጊዜ በሶስት ጋብቻን በጥሶ ፍቺ ማወጅ የተከለከለ መሆኑን፤
30. ለሶስተኛ ጊዜ የተፈታች ወደ ፈታት ባሏ መመለስ የምትችለው ሌላ ባል አግብታ ከተፈታች ወይም ሲሞትባት እንደሆነ፤
31. ሴት ባሏን የመምረጥና የጋብቻ ሕይወቷን ካልተስማማት እንደ ወንዱ ጋብቻውን የማፍረስ መብት እንዳላት ጋብቻውንም ማፍረስ የምትችለው ወንዱ ለጋብቻው ጥሎሽ የሰጣትን ንብረት ተመላሽ አድርጋ እንደሆነ፤
32. ሚስቱን በአንድ ወይም በሁለት የፈታ ወንድ ሚስቱን ለመበቀል በማሰብ ጋብቻውን መቀጠል እንደሌለበት፤
33. የአላህን ህግጋት መጫወቻ ማድረጉ ተገቢ እንዳልሆነ፤
34. የአላህን ፀጋ በቃል ማውሳትና በልብ መያዝ እርሱን በስውርም ሆነ በይፋ መፍራትና ሁሌም አላህ መጠበቅ ተገቢ እንደሆነ፤
35. ሴት ልጅ በኢዳዋ ላይ እያለች ወደ ትዳሯ ለመመለስ በምታስብበት ጊዜ እንቅፋት መሆን እንደማይገባ፤
36. ጋብቻን ለመፈፀም ሴት ልጅ ወኪል ማቅረቧ ተገቢ እንደሆነ፤
37. በልቡ ውስጥ እምነት ያለው ሰው ምክርና ተግሳፅ ከስህተቱ እንዲታረም ሊያደርገው እንደሚችል፤
38. ከሁለት ዓመት በኋላ ያለ ማጥባት በሸሪዓ ግምት ውስጥ እንደማይገባ፤
39. አነስተኛው የማጥቢያ ዘመን ስድስት ወር መሆኑንና በእነዚህም ወራቶች ውስጥ ልጅ ሊወለድ እንደሚችል፤
40. ያልተፈታች ሴት ከቀለብና ከልብስ ሌላ ምንም ነገር መስጠት እንደማይገደድ፤
41. የሴት ዘመድ የሆነ ያልተፈቀደ ነገር እንዳትሰራ መከልከል የተፈቀደ ነገር እንድትሰራ ሊመክራት ብሎም ሊያስገድዳት እንደሚገባ እንማራለን።

وَٱلَّذِينَ يُتَوَفَّوْنَ مِنكُمْ وَيَذَرُونَ أَزْوَٰجًا يَتَرَبَّصْنَ بِأَنفُسِهِنَّ أَرْبَعَةَ أَشْهُرٍ وَعَشْرًا ۖ فَإِذَا بَلَغْنَ
أَجَلَهُنَّ فَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ فِيمَا فَعَلْنَ فِىٓ أَنفُسِهِنَّ بِٱلْمَعْرُوفِ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ٢٣٤

**234.** (ወንዶች ሆይ!) እነዚያ ከናንተ ውስጥ የሚሞቱና ሚስቶችን የሚተው (ሚስቶቻቸው) በራስ ተነሳሽነት ጭምር አራት ወር ከአስር ቀናት ከጋብቻ ይታገሱ። ጊዜያቸውንም በጨረሱ ጊዜ በራሳቸው ተነሳሽነት በሚፈጽሙት ሕጋዊ ተግባር በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። አላህ የምትሰሩትን ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው።

وَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ فِيمَا عَرَّضْتُم بِهِۦ مِنْ خِطْبَةِ ٱلنِّسَآءِ أَوْ أَكْنَنتُمْ فِىٓ أَنفُسِكُمْ ۚ
عَلِمَ ٱللَّهُ أَنَّكُمْ سَتَذْكُرُونَهُنَّ وَلَـٰكِن لَّا تُوَاعِدُوهُنَّ سِرًّا إِلَّآ أَن تَقُولُوا۟ قَوْلًا مَّعْرُوفًا ۚ
وَلَا تَعْزِمُوا۟ عُقْدَةَ ٱلنِّكَاحِ حَتَّىٰ يَبْلُغَ ٱلْكِتَـٰبُ أَجَلَهُۥ ۚ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِىٓ
أَنفُسِكُمْ فَٱحْذَرُوهُ ۚ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ حَلِيمٌ ﴿٢٣٥﴾

**235.** (ወንዶች ሆይ!) ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶች የጋብቻ (አሽሙር) ፍንጭ በመስጠታችሁ ወይም እንዲህ ዓይነቱን ሀሳብ በውስጣችሁ በማሰባችሁ ምክንያት በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። አላህ እናንተ በእርግጥ እንዲህ ዓይነቱን ሀሳብ እንደምታስተናግዱ ቀድሞውኑ ያውቃል። ስለዚህ (አሽሙር) ፍንጭ መስጠትንና ማሰብን ፈቀደላችሁ። ግና በሕግ የታወቀን ጨዋ ንግግር የምትነጋገሩ ካልሆናችሁ በስተቀር ለትዳር እንደምትፈልጓቸው የተፃፈው የኢዳ ጊዜው እስከሚደርስ ድረስ ጋብቻን ለመዋዋል ቁርጥ ሀሳብ አታድርጉ። አላህ በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉን ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑን እወቁ። ተጠንቀቁም አላህ መህሪና ታጋሽ መሆኑንም እወቁ።

لَّا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ إِن طَلَّقْتُمُ ٱلنِّسَآءَ مَا لَمْ تَمَسُّوهُنَّ أَوْ تَفْرِضُوا۟ لَهُنَّ فَرِيضَةً ۚ وَمَتِّعُوهُنَّ
عَلَى ٱلْمُوسِعِ قَدَرُهُۥ وَعَلَى ٱلْمُقْتِرِ قَدَرُهُۥ مَتَـٰعًۢا بِٱلْمَعْرُوفِ ۖ حَقًّا عَلَى ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٢٣٦﴾ وَإِن
طَلَّقْتُمُوهُنَّ مِن قَبْلِ أَن تَمَسُّوهُنَّ وَقَدْ فَرَضْتُمْ لَهُنَّ فَرِيضَةً فَنِصْفُ مَا فَرَضْتُمْ إِلَّآ أَن
يَعْفُونَ أَوْ يَعْفُوَا۟ ٱلَّذِى بِيَدِهِۦ عُقْدَةُ ٱلنِّكَاحِ ۚ وَأَن تَعْفُوٓا۟ أَقْرَبُ لِلتَّقْوَىٰ ۚ وَلَا تَنسَوُا۟ ٱلْفَضْلَ
بَيْنَكُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿٢٣٧﴾

**236-237.** (ባሎች ሆይ!) ሴቶችን ግንኙነት ከማድረግ በፊት ወይም ለእነርሱ መህርን ሳትወስኑላቸው ብትፈቷቸው በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም። ነገር ግን ሀብታምም ደሃም እንደየአቅማቸው ይካሷቸው። ይህ አቅምን መሰረት ያደረገ ካሳ በቅን ሰዎች ላይ የተደነገገ ህግ ነው። (ባሎች ሆይ!) ለሚስቶቻችሁ መህርን የወሰናችሁላቸው ስትሆኑ ሳትገናኟቸው በፊት ብትፈቷቸው ራሳቸው ይቅር ካላሉ ወይም ያ የጋብቻ ውል በእጁ የሆነ ባል ይቅር ካላለ በስተቀር ከወሰናችሁት ግማሹን መስጠት ግድ ሆኖባችኋል። ሁላችሁም ይቅር መባባላችሁ ወደ አላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ተግባር ነው። አንዱ ለሌላው በጎ መዋልን አይዘንጋ። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

حَٰفِظُواْ عَلَى ٱلصَّلَوَٰتِ وَٱلصَّلَوٰةِ ٱلۡوُسۡطَىٰ وَقُومُواْ لِلَّهِ قَٰنِتِينَ ٢٣٨ فَإِنۡ خِفۡتُمۡ فَرِجَالًا
أَوۡ رُكۡبَانٗاۖ فَإِذَآ أَمِنتُمۡ فَٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ كَمَا عَلَّمَكُم مَّا لَمۡ تَكُونُواْ تَعۡلَمُونَ ٢٣٩

**238-239.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ሶላቶችን በተለይ መካከለኛይቱን (የአስርን) ሶላት ወቅታቸውንና ስርዓታቸውን ጠብቃችሁ ስገዱ። በሙሉ ታዛዥነትም ለአላህ ቁሙ። የደህንነት ስጋት ሲኖር በእግር እየሄዳችሁም ሆነ ተሳፍራችሁ* ስገዱ። ሰላም ሲሰፍን በተለመደው ሥርዓት ታውቁት ያልነበራችሁትን እንዳሳወቃችሁ ሁሉ አላህን በአግባቡ አውሱ (ስገዱ)።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የፍራቻ ሶላትን አስመልክቶ፡- «በዛቲ አርሪቃዕ» ጦርነት ላይ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጋር ከሰገዱት ሰዎች ሳሊሕ ብኑ ኸውዋት እንዳስተላለፉት የተወሰነው የጦር ሃይል ከአላህ መልዕክተኛ ኋላ በሰልፍ በመቆም ሶላት ሲጀምር የተወሰነው የጦር ሃይል ፊቱን ወደ ጠላት አቅጣጫ አዞሮ ቆሞ ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) አንድ ረከዐ ከመጀመሪያዎቹ ጋር ከሰገዱ በኋላ ለሁለተኛው ረከዐ ቆሙ። ይህ የመጀመሪያው የጦር ኃይል የቀራቸውን አንድ ረከዐህ ለብቻቸው ሰገዱና ሳይጨርሱ ሁለተኛው የጦር ኃይል ወደ ነበረበት ተመለሰ። ሁለተኛው የጦር ኃይል ከአላህ መልዕክተኛ ኋላ በሰልፍ በመቆም አንድ ረከዐህ አብረው ሰገዱና የአላህ መልዕክተኛ ሶላታቸውን ሳያጠናቅቁ ለረዥም ጊዜ ተቀመጡ። ሁለተኛው የጦር ኃይል የቀራቸውን ሁለተኛ ረከዐህ ሰገዱና ተቀመጡ። ከዚያም የመጀመሪያው የጦር ኃይል ጋር ተቀላቅለው ሶላታቸውን በአንድነት አጠናቀቁ።

ከላሟ ምዕራፍ (238) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በሶላት ውስጥ እርስ በራሳቸው ይነጋገሩ ስለነበር እነሱን ለመከልከል ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሰድስቱ መፅሐፍ፤ አህመድና ሱዩጢ)

وَٱلَّذِينَ يُتَوَفَّوۡنَ مِنكُمۡ وَيَذَرُونَ أَزۡوَٰجٗا وَصِيَّةٗ لِّأَزۡوَٰجِهِم مَّتَٰعًا إِلَى ٱلۡحَوۡلِ غَيۡرَ إِخۡرَاجٖۚ
فَإِنۡ خَرَجۡنَ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡكُمۡ فِي مَا فَعَلۡنَ فِيٓ أَنفُسِهِنَّ مِن مَّعۡرُوفٖۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ
حَكِيمٞ ٢٤٠ وَلِلۡمُطَلَّقَٰتِ مَتَٰعُۢ بِٱلۡمَعۡرُوفِۖ حَقًّا عَلَى ٱلۡمُتَّقِينَ ٢٤١ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمۡ
ءَايَٰتِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ٢٤٢

**240-242.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እነዚያ ከናንተ ውስጥ ሚስቶችን ትተው የሚሞቱ ለሚስቶቻቸው ከየቤቶቻቸው የማይወጡ ሆነው ሳለ ዓመት ድረስ ወጪቸው እንዲሸፈን መናዘዝ ይኖርባቸዋል። ሚስቶች በፈቃዳቸው ከቤት ቢወጡ ግን ደንብ ጠብቀውና ኃላፊነትን ወስደው በሰሩት ጉዳይ ላይ በሟች ዘመዶች ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነው።* ለተፈቱ ሴቶች ሁሉ በፍችው ባል ችሎታ መጠን ዳረጎት (የገንዘብ ድጎማ) ይሰጣቸዋል። ይህ አላህን በሚፈሩ ሰዎች ሁሉ ላይ ተደንግጓል። ልክ እንደዚሁ አላህ አናቅፅን ታውቁ ዘንድ ለእናንተ ያብራራላችኋል።

✷ ይህ ህግ በዚሁ ምዕራፍ በ (234) ኛው አንቀፅ ላይ በተደነገገው በአራት ወር ከአስር ቀን ተቀይሯል።

ከላሟ ምዕራፍ (241) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዚሁ ምዕራፍ (236) ኛው ላይ ያለው የቁርአን አንቀፅ ሲወርድ አንዱ ተነስቶ ኸይር ነገርን ከፈለኩኝ አደርጋለሁ ካልፈለኩኝ ማንም አያስገድደኝም በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

۞ أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ خَرَجُواْ مِن دِيَٰرِهِمْ وَهُمْ أُلُوفٌ حَذَرَ ٱلْمَوْتِ فَقَالَ لَهُمُ ٱللَّهُ مُوتُواْ ثُمَّ أَحْيَٰهُمْۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَذُو فَضْلٍ عَلَى ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَشْكُرُونَ ﴿٢٤٣﴾ وَقَٰتِلُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱعْلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٢٤٤﴾

**243-244.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደነዚያ እነርሱ ብዙ ሺህ ሆነው ሞትን በመፍራት ከሀገሮቻቸው የወጡ ሰዎችን ታሪክ አላየህምን (አላወቅክምን?) አላህ ለእነርሱ «ሞትን» ቅመሱ አላቸው። ሞቱም። ከዚያ እንደገና ነፍስ ዘራባቸው። አላህ ለሰዎች ሁሉ እጅግ ቸር ነው። ይሁንና አብዛሀኞቹ ሰዎች አያመሰግኑም። (ሙስሊሞች ሆይ!) የአላህን መንገድ በመርዳት ላይ ተጋደሉ። አላህ ለሚባለው ሁሉ ነገር ሰሚ፤ ለሚፈፅመው ሁሉ ነገር ሁሉ አዋቂ መሆኑንም እወቁ።

مَّن ذَا ٱلَّذِي يُقْرِضُ ٱللَّهَ قَرْضًا حَسَنًا فَيُضَٰعِفَهُۥ لَهُۥٓ أَضْعَافًا كَثِيرَةًۚ وَٱللَّهُ يَقْبِضُ وَيَبْصُۜطُ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿٢٤٥﴾

**245.** ያለአላህ መልካም ብድርን የሚያበድርና አላህ እጥፍ ድርብ አድርጎ እንዲከፍለው የሚሻ ማን ነው? አላህ ለፈለገው ሰው ገቢን ያጠብበታል፤ ለፈለገው ደግሞ ያሰፋለታልም። ወደ እርሱ ብቻ ትመለሳላችሁ።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (233-245) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፡-**

1. ወላጅ እናት በመጀመሪያ የወሊድ ወራት (ልጇን) የማጥባት ግዴታ እንደተጣለባት፤
2. የማጥቢያ አድሜ ሁለት ዓመት እስኪሞላው ድረስ እንደሚዘልቅ፤
3. ወላጅ እናት ልጇን በማጥባቷ ከአባቱ ገንዘብ መጠየቅ እንደምትችል፤
4. አባት ልጁን በሌላ ሴት ጡት የማስጠባት መብት እንዳለው፤
5. ከግንኙነት በኋላ ባሏ የሞተባት ለሞራል መጠበቂያ እስከ አንድ አመት ድረስ በባሏ ቤት የመኖር መብት እንደላት፤
6. የተፈታች ሴት ያላት መብት እስከምን እንደሆነ፤
7. አላህ ህግጋትን በማሳወቅ በማብራራት ለሕዝበ ኢስላም የዋለው ውለታ እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ፤
8. ባሏ የሞተባት ሴት ከሞተበት ዕለት አንስቶ አራት ወራት ከአስር ቀናት እስኪሞላ ድረስ የኢዳዋ ጊዜ መሆኑንና በእነዚህ የኢዳዋ ቀናቶች መጋጌጥ፤ መኳኳል እና ሽቶ መቀባት እንደሌለባት፤

9. ሌላ ባል ለማግባት መደራደር የተከለከለ መሆኑን፤
10. ከአቅሟ በላይ የሆነ ችግር ካላጋጠማት በስተቀር በሷ ከሞተበት ቤት መውጣትም የማይገባት መሆኑን፤
11. ባሏ ሙቶባት ኢዳዋን እየቆጠረች የምትገኝን ሴት ከመጠቆምና አዝማሚያን ከማመልከት በስተቀር በይፋ ማጨት የተከለከለ መሆኑን፤
12. እንዲሁም ከእሷ ጋር ጋብቻ መፈፀምም የተከለከለ መሆኑን፤
13. የሞራል መጠበቂያ ስጦታ መህር ሳይወሰን ለተገባች ሴት ግዴታ መሆኑ፤
14. በሁሉም ነገር አላህን መፍራት ግዴታ መሆኑን፤
15. በኢዳ ላይ ያሉ ሴቶች በሚያጠፉት ጥፋት ቤተ ዘመድ እንደማይጠየቅ፤
16. ልጆች መጠራት ያለባቸው በአባቶቻቸው መሆኑን፤
17. ህፃንን ጡት ለማስጣል ከሁለት አመት በፊት ከሆነ በአባትና በእናት ምክክርና ስምምነት መሆን እንዳለበት፤
18. ለትዳሩ የሚጎዳ ችግር ካለ ከግንኙነት በፊት መፍታት እንደሚቻል፤
19. መህሯ ተነግሮ የተገባች ሴት ከግንኙነት በፊት ከተፈታች የመህሯ ግማሽ እንደሚሰጣት
20. መህሯ ያልተወሰነላት ሴት ካገባት ባል ጋር ግኙኙነት ከማድረጓ በፊት ብትፈታ ሞራል መጠበቂ ብቻ እንደሚገባት፤
21. የአምስት አውቃት ሶላቶችን ጠብቆ ከሙሉ ሥርዓቱ ጋር መፈፀም እንደሚገባ፤ በተለይ የአስርን ሶላት ጠብቆ መስገድ ልዩ ትኩረት እንደሚሰጠው፤ በሶላት ውስጥ ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን በሙሉ ከመናገር መቆጠብ እንደሚገባ፤
22. በመንገድ ላይ ተጓዥ የሆነ ሰው ቆሞ መስገድ ለጠላት ጥቃት ያጋልጠኛል ብሎ ከሰጋ በእግሩ እየሄደም ሆነ በመጓጓዝ ላይ ሆኖ መስገድ እንደሚችል፤
23. ወደ አንድ ሀገር የወረርሽኝ በሽታ ከገባ ከዚያ ወረርሽን ሽሽት ሀገር ለቆ መሄድ ክልክል መሆኑን፤
24. የአላህን ፀጋዎች ማስታወስ ግዴታ ስለመሆኑ፤
25. ለኢስላም ክብርና ልቅና ሲባሉ የሚከፈሉ መስዋእቶች በሙሉ በአላህ ዘንድ ታላቅ ዋጋ የሚሰጣቸው መሆኑን፤
26. አላህ ለክቶ በሰጠው ሲሳይ ተብቃቅቶ መኖር ምን ያህል ከፍ ያለ ምንዳ እንዳለው፤
27. ሰዎችም ሆኑ ሌሎች ፍጡራን መጨረሻቸው ወደ አላህ መሆኑን፤
28. አላህ ገድሎ ማንሳት እንደማያቅተው በዚህ አለም በዱንያ ያሳቸው ተዐምሮች እንደነበሩ፤
29. አላህ አያሌ ተዐምራትን ቢያሳይም እንኳን ብዙ ሰዎች እውነትን ለመረዳት አለመታደላቸውን እንማራለን።

أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلۡمَلَإِ مِنۢ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ مِنۢ بَعۡدِ مُوسَىٰٓ إِذۡ قَالُواْ لِنَبِيّٖ لَّهُمُ ٱبۡعَثۡ لَنَا مَلِكٗا
نُّقَٰتِلۡ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِۖ قَالَ هَلۡ عَسَيۡتُمۡ إِن كُتِبَ عَلَيۡكُمُ ٱلۡقِتَالُ أَلَّا تُقَٰتِلُواْۖ قَالُواْ
وَمَا لَنَآ أَلَّا نُقَٰتِلَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَقَدۡ أُخۡرِجۡنَا مِن دِيَٰرِنَا وَأَبۡنَآئِنَاۖ فَلَمَّا كُتِبَ عَلَيۡهِمُ
ٱلۡقِتَالُ تَوَلَّوۡاْ إِلَّا قَلِيلٗا مِّنۡهُمۡۚ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِٱلظَّٰلِمِينَ ٢٤٦

**246.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከኢስራኤል ልጆች ከሙሳ ዘመን በኋላ ወደ ነበሩት የቤተ-ኢስራኢል ታላላቅ ሰዎች ተልኮላቸው ለነበረው ለነብያቸው «ለእኛ ንጉስን» ሹምልን እና በአላህ መንገድ እንዋጋ ባሉ ጊዜ የሆነውን አላገናዘብክምን (አላየህምን)? እሱም መዋጋት ቢፃፍባችሁ አትዋጉ ይሆናል አላቸው። እነርሱም ከአገሮቻችንና ከልጆቻችን ተባረናል። ታዲያ በአላህ መንገድ የማንዋጋበት ምን ምክንያት አለን? አሉ። በእነርሱ ላይ መዋጋት በተፃፈባቸው ጊዜ ግን ከእነርሱ ጥቂቶች ሲቀሩ ከመዋጋት አፈገፈጉ። አላህ አጥፊዎችን ሁሉ በሚገባ ያውቃቸዋል።

وَقَالَ لَهُمۡ نَبِيُّهُمۡ إِنَّ ٱللَّهَ قَدۡ بَعَثَ لَكُمۡ طَالُوتَ مَلِكٗاۚ قَالُوٓاْ أَنَّىٰ يَكُونُ لَهُ ٱلۡمُلۡكُ عَلَيۡنَا
وَنَحۡنُ أَحَقُّ بِٱلۡمُلۡكِ مِنۡهُ وَلَمۡ يُؤۡتَ سَعَةٗ مِّنَ ٱلۡمَالِۚ قَالَ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰهُ عَلَيۡكُمۡ وَزَادَهُۥ
بَسۡطَةٗ فِي ٱلۡعِلۡمِ وَٱلۡجِسۡمِۖ وَٱللَّهُ يُؤۡتِي مُلۡكَهُۥ مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ وَٰسِعٌ عَلِيمٞ ٢٤٧

**247.** ነብያቸው ለነሱ «አላህ ጧሉትን ንጉስ አድርጎ በእርግጥ ላከላችሁ» አላቸው። እነርሱም፡- እኛ ከእርሱ ይልቅ ለንግስና ተገቢዎች ስንሆን ሰፊ ሀብትም ያልተሰጠ ሲሆን እርሱ በእኛ ላይ እንዴት ይነግሣል? አሉ። ነብያቸውም፡- አላህ በእናንተ ላይ መረጠው በእውቀትና ጥንካሬ አጎናጽፎታል። አላህ ንግስናውን ለሚሻለት ሰው ይሰጣል። አላህ ችሮታው ሰፊና አዋቂ ነው አላቸው።

وَقَالَ لَهُمۡ نَبِيُّهُمۡ إِنَّ ءَايَةَ مُلۡكِهِۦٓ أَن يَأۡتِيَكُمُ ٱلتَّابُوتُ فِيهِ سَكِينَةٞ مِّن رَّبِّكُمۡ وَبَقِيَّةٞ مِّمَّا
تَرَكَ ءَالُ مُوسَىٰ وَءَالُ هَٰرُونَ تَحۡمِلُهُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لَّكُمۡ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٢٤٨

**248.** በተጨማሪም ነብያቸው እንዲህ አላቸው የንግስናው ምልክት መላእክት የሚሸከሙት ሳጥን ወደ እናንተ ይመጣል። በውስጡ ለናንተ እርጋታን የሚፈጥርና የሙሳ እና የሀሩን ቤተሰብ ቅርስም ይገኝበታል። በዚህም ሁኔታ አማኞች ከሆናችሁ ከባድ ተዐምር አለላችሁ።

فَلَمَّا فَصَلَ طَالُوتُ بِٱلۡجُنُودِ قَالَ إِنَّ ٱللَّهَ مُبۡتَلِيكُم بِنَهَرٖ فَمَن شَرِبَ مِنۡهُ فَلَيۡسَ مِنِّي وَمَن لَّمۡ
يَطۡعَمۡهُ فَإِنَّهُۥ مِنِّيٓ إِلَّا مَنِ ٱغۡتَرَفَ غُرۡفَةَۢ بِيَدِهِۦۚ فَشَرِبُواْ مِنۡهُ إِلَّا قَلِيلٗا مِّنۡهُمۡۚ فَلَمَّا جَاوَزَهُۥ هُوَ
وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَعَهُۥ قَالُواْ لَا طَاقَةَ لَنَا ٱلۡيَوۡمَ بِجَالُوتَ وَجُنُودِهِۦۚ قَالَ ٱلَّذِينَ يَظُنُّونَ أَنَّهُم مُّلَٰقُواْ
ٱللَّهِ كَم مِّن فِئَةٖ قَلِيلَةٍ غَلَبَتۡ فِئَةٗ كَثِيرَةَۢ بِإِذۡنِ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ مَعَ ٱلصَّٰبِرِينَ ٢٤٩

249. ጧሉትም በሰራዊቱ ታጅቦ በወጣ ጊዜ «አላህ በወንዝ ውሃ ይፈትናችኋል። እናም ከእርሱ የጠጣ ሰው ሁሉ ከእኔ አይደለም። እሱን ያልቀመሰው ሰው ግን በእጁ አንድ እፍኝ ያህል የዘገነ ሰው ብቻ ሲቀር እርሱ ከእኔ ነው» አለ። ከእነርሱም መካከል ጥቂቶች ሲቀሩ ከእርሱ ጠጡ። እርሱና እነዚያ ከእርሱ ጋር ያመኑት ወንዙን ባለፉት ጊዜ፡- ጃሉትን (ጎልያድን) እና ሰራዊቱን ለመዋጋት በቂ ችሎታና ጥንካሬ የለንም አሉት። እነዚያ እነርሱ ከአላህ ጋር እንደሚገናኙ የሚያረጋግጡት ግን ጥቂት ጭፍራ በአላህ ፈቃድ ብዙውን ጭፍራ ያሸነፈበት አጋጣሚ ብዙ ነው። አላህ ከታጋሾች ሁሉ ጋር ነውና አሉ።

وَلَمَّا بَرَزُواْ لِجَالُوتَ وَجُنُودِهِۦ قَالُواْ رَبَّنَآ أَفۡرِغۡ عَلَيۡنَا صَبۡرٗا وَثَبِّتۡ أَقۡدَامَنَا وَٱنصُرۡنَا عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿٢٥٠﴾ فَهَزَمُوهُم بِإِذۡنِ ٱللَّهِ وَقَتَلَ دَاوُۥدُ جَالُوتَ وَءَاتَىٰهُ ٱللَّهُ ٱلۡمُلۡكَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَعَلَّمَهُۥ مِمَّا يَشَآءُۗ وَلَوۡلَا دَفۡعُ ٱللَّهِ ٱلنَّاسَ بَعۡضَهُم بِبَعۡضٖ لَّفَسَدَتِ ٱلۡأَرۡضُ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ ذُو فَضۡلٍ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٢٥١﴾

250-251. ለጃሉትና ለሰራዊቱ በተሰለፉም ጊዜ፡- ጌታችን ሆይ! ትግስትን ለግሰን። እግሮቻችንን አጽናልን። በከሓዲያን ሕዝቦችም ላይ እርዳን አሉ። እናም በአላህ ፈቃድ ድል መቷቸው። ነብዩ ዳውድም ጃሉትን ገደለ። ለዳውድ ንግሥናን፤ ጥበብን እና ነብይነትን አላህ ሰጣቸው። ከሚሻው ነገር ሁሉ አሳወቀው። አላህ ሰዎችን ከፊላቸውን በከፊሉ መመለሱ (መከላከሉ) ባልነበረ ኖሮ ምድር በጠቅላላ በተበላሸች ነበር። ግን አላህ በዓለማት ላይ የችሮታ ባለቤት ነው።

تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱللَّهِ نَتۡلُوهَا عَلَيۡكَ بِٱلۡحَقِّۚ وَإِنَّكَ لَمِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿٢٥٢﴾

252. እነዚህ አንቀፆች በእውነት በአንተ ላይ የምናነባቸው ሲሆኑ የአላህ አንቀፆች ናቸው። አንተም በእርግጥ ከመልዕክተኞቹ መካከል አንዱ ነህ።

۞تِلۡكَ ٱلرُّسُلُ فَضَّلۡنَا بَعۡضَهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۘ مِّنۡهُم مَّن كَلَّمَ ٱللَّهُۖ وَرَفَعَ بَعۡضَهُمۡ دَرَجَٰتٖۚ وَءَاتَيۡنَا عِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ٱلۡبَيِّنَٰتِ وَأَيَّدۡنَٰهُ بِرُوحِ ٱلۡقُدُسِۗ وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ مَا ٱقۡتَتَلَ ٱلَّذِينَ مِنۢ بَعۡدِهِم مِّنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَٰتُ وَلَٰكِنِ ٱخۡتَلَفُواْ فَمِنۡهُم مَّنۡ ءَامَنَ وَمِنۡهُم مَّن كَفَرَۚ وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ مَا ٱقۡتَتَلُواْ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَفۡعَلُ مَا يُرِيدُ ﴿٢٥٣﴾

253. *እነዚህን መልዕክተኞች ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ አበለጥን። ከእነርሱ መካከል አላህ ያነጋገረው አለ። ከፊሎቻቸውንም በደረጃ ከሌሎች ከፍ አድርጓል። የመርየምን ልጅ ዒሳንም ግልፅ ተዐምራት ሰጠነው። በቅዱስ መንፈስም (በመላኩ ጂብሪል) አበረታነው። አላህ በፈለገ ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ በኋላ መረጃው ከመጣላቸው በኋላ እርስ በእርሳቸው ባልተዋጉ ነበር። ግን ተለያዩ። በመሆኑም ከመሀከላቸው ትክክለኛ አማኝ ክፍል አለ። ከመሀከላቸዉም ከሃዲ አለ። አላህ በፈለገ ኖሮ እርስ በእርሳቸው ባልተዋጉ ነበር። አላህ ግን የሚሻውን ሁሉ ይሰራል።

✶ ክፍል ሶስት

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَنفِقُواْ مِمَّا رَزَقْنَـٰكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ يَوْمٌ لَّا بَيْعٌ فِيهِ وَلَا خُلَّةٌ وَلَا شَفَـٰعَةٌ ۗ وَٱلْكَـٰفِرُونَ هُمُ ٱلظَّـٰلِمُونَ ﴿٢٥٤﴾

254. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ያ ንግድ፤ ወዳጅነትም ሆነ ምልጃ የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ ለግሱ። በዳዩች ማለት ከሐዲያን ናቸው።

ٱللَّهُ لَآ إِلَـٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْحَىُّ ٱلْقَيُّومُ ۚ لَا تَأْخُذُهُۥ سِنَةٌ وَلَا نَوْمٌ ۚ لَّهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۗ مَن ذَا ٱلَّذِى يَشْفَعُ عِندَهُۥٓ إِلَّا بِإِذْنِهِۦ ۚ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ ۖ وَلَا يُحِيطُونَ بِشَىْءٍ مِّنْ عِلْمِهِۦٓ إِلَّا بِمَا شَآءَ ۚ وَسِعَ كُرْسِيُّهُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ ۖ وَلَا يَـُٔودُهُۥ حِفْظُهُمَا ۚ وَهُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْعَظِيمُ ﴿٢٥٥﴾

255. አላህ ከእርሱ በስተቀር ሌላ ትክክለኛ አምላክ የለም። አላህ ሕያው፣ በራሱ የተብቃቃ ነው። ማንጎላጀትም ሆነ እንቅልፍ አትይዘውም። በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። ያ እርሱ ዘንድ በፍቃዱ ቢሆን እንጂ የሚያማልድ ማን ነው? (ከፍጡራን) ሁሉ በፊታቸው ያለውንና ከኋላቸው ያለውን ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። በሻው ነገር እንጂ ከእውቀቱ (ፍጡራን) በምንም ነገር አያካብቡም። (አያውቁም) መንበሩ የሰማያትንና የምድርን ስፋት ይበልጣል። ጥበቃቸውም አያቅተውም። እርሱ የሁሉ የበላይና ታላቅ ነው።

لَآ إِكْرَاهَ فِى ٱلدِّينِ ۖ قَد تَّبَيَّنَ ٱلرُّشْدُ مِنَ ٱلْغَىِّ ۚ فَمَن يَكْفُرْ بِٱلطَّـٰغُوتِ وَيُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱسْتَمْسَكَ بِٱلْعُرْوَةِ ٱلْوُثْقَىٰ لَا ٱنفِصَامَ لَهَا ۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٢٥٦﴾

256. በሃይማኖት ማስገደድ የለም። ቅኑ መንገድ ከጠማማው መንገድ በእርግጥ ተገለጠ። በጣኦት (ባዕድ አምልኮ) የሚክድና በአላህ የሚያምን ሰው ሁሉ የማትበጠስ ጠንካራ ገመድን ጨብጧል። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ የሚፈፅመውን ሁሉ ነገር አዋቂ ነውና።

ٱللَّهُ وَلِيُّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ يُخْرِجُهُم مِّنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ ۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ أَوْلِيَآؤُهُمُ ٱلطَّٰغُوتُ يُخْرِجُونَهُم مِّنَ ٱلنُّورِ إِلَى ٱلظُّلُمَٰتِ ۗ أُو۟لَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٢٥٧﴾

257. አላህ የእነዚያ ያመኑት ሰዎች ወዳጅ ነው። ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል። እነዚያ የካዱት ሰዎች ግን ረዳቶቻቸው ጣኦታት ናቸው። ከብርሃን ወደ ጨለማ ይመሯቸዋል። እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِى حَآجَّ إِبْرَٰهِۦمَ فِى رَبِّهِۦٓ أَنْ ءَاتَىٰهُ ٱللَّهُ ٱلْمُلْكَ إِذْ قَالَ إِبْرَٰهِۦمُ رَبِّىَ ٱلَّذِى يُحْىِۦ وَيُمِيتُ قَالَ أَنَا۠ أُحْىِۦ وَأُمِيتُ ۖ قَالَ إِبْرَٰهِۦمُ فَإِنَّ ٱللَّهَ يَأْتِى بِٱلشَّمْسِ مِنَ ٱلْمَشْرِقِ فَأْتِ بِهَا مِنَ ٱلْمَغْرِبِ فَبُهِتَ ٱلَّذِى كَفَرَ ۗ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢٥٨﴾

258. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደዚያ ያንን አላህ ንግስናን ስለ ሰጠውና ኢብራሂምን በጌታው ጉዳይ ክርክር ስለ ከፈተው ሰው (ታሪክ) መረጃ አላየህምን? ኢብራሂም፡- «ጌታዬ ያ የፈለገውን ሕያው የሚያደርግና የፈለገውን የሚገድል ነው» ሲለው እኔም የፈለኩትን ህያው አደርጋለሁ፤ የፈለኩትን እገድላለሁ አለ። ኢብራሂምም፡- አላህ ፀሐይን በምስራቅ በኩል ያወጣል። አንተ ከምዕራብ በኩል አስኪ አምጣት አለው። ያም የካደ ሰው ዋለለ (መልስ አጣ)። አላህ ግፈኛ ሕዝቦችን ሁሉ አይመራምና።

أَوْ كَٱلَّذِى مَرَّ عَلَىٰ قَرْيَةٍ وَهِىَ خَاوِيَةٌ عَلَىٰ عُرُوشِهَا قَالَ أَنَّىٰ يُحْىِۦ هَٰذِهِ ٱللَّهُ بَعْدَ مَوْتِهَا ۖ فَأَمَاتَهُ ٱللَّهُ مِا۟ئَةَ عَامٍ ثُمَّ بَعَثَهُۥ ۖ قَالَ كَمْ لَبِثْتَ ۖ قَالَ لَبِثْتُ يَوْمًا أَوْ بَعْضَ يَوْمٍ ۖ قَالَ بَل لَّبِثْتَ مِا۟ئَةَ عَامٍ فَٱنظُرْ إِلَىٰ طَعَامِكَ وَشَرَابِكَ لَمْ يَتَسَنَّهْ ۖ وَٱنظُرْ إِلَىٰ حِمَارِكَ وَلِنَجْعَلَكَ ءَايَةً لِّلنَّاسِ ۖ وَٱنظُرْ إِلَى ٱلْعِظَامِ كَيْفَ نُنشِزُهَا ثُمَّ نَكْسُوهَا لَحْمًا ۚ فَلَمَّا تَبَيَّنَ لَهُۥ قَالَ أَعْلَمُ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٢٥٩﴾

**259.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወይም ያንን ሙሉ በሙሉ በፈራረሰች ከተማ ያለፈውን ሰው ተሞክሮ አላገናዘብክምን? «ይህችን ከተማ ከሞተች በኋላ አላህ እንዴት ሕያው ያደርጋታል? አለ። ከዚያ አላህ ገደለውና መቶ ዓመትን አቆየው። ከዚያ አስነሳው ምን ያህል ቆየህ? አለው። አንድ ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆይቻለሁ አለ። ይልቁንም መቶ ዓመት ነው የቆየኸው። ወደ ምግብህና ወደ መጠጥህም ተመልከት። አንዱም አልተለወጠም። ወደ አህያህም ተመልከት። ለሰው ልጅም ተዐምር ልናደርግህ ዘንድ (ይህንን ሰራን)፤ ወደ አፅሞችም እንዴት እንደምናስነሳት ከዚያ ስጋን እንዴት እንደምናለብሳት ተመልከት አለው። ለእርሱም ማስረጃ በገለፀለት ጊዜ «አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መሆኑን አውቃለሁ» አለ!።

**ከላሟ ምዕራፍ አንቀፅ (246-259) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ጂሃድን ለማወጅም ሆነ ለመምራት የሚችለው ሕጋዊ የሙስሊም ሕዝብ መሪ እንደሆነ፤
2. ለሙስሊሙ ህዝብ መሪ ለመሆን ጥልቅ እውቀትን መጨበጥ የአዕምሮና የሰውነት ጤንነት የተሟላ መሆን እንደሚገኑበት፤
3. መሪው ለጂሃድ አዋጅን ከማውጣት ጦርነቱን ስትራቴጂ መንደፍ እንደሚገባ፤
4. የጂሃድ ዓላማውና ጥቅሙ ግፍን፤ በደልንና ጭቆናን አስወግዶ ፍትሕንና ሰላምን ለማስፈን እንደሆነ፤
5. ድል አድራጊነት በአላህ ፈቃድ ብቻ እንጂ በኃይልና በጉልበት እንዳልሆነ፤
6. በምድር ላይ የሚከሰቱ የተለያዩ አይነት ውድቀቶች የአላህን ህግ በመጣስ ምክንያት የሚከሰቱ መሆኑን፤
7. ሁሉም ነብያት የተመረጡ የአላህን ተልዕኮ ያነገቡ የአላህ ክቡር ባሪያዎች ቢሆንም በመሀከላቸው እንደሚበላለጡ፤
8. አላህ እንደሚናገርና ከነብያት መካከልም በቀጥታ ያነጋገረው ነብይ እንዳለ ያም ነብዩሏህ ሙሳ መሆናቸውን፤
9. የዚህ ዓለም መንፈሳዊውም ሆነ ቁሳዊ ነገሮች ሁሉ የሚቀመሩትና የሚከናወኑት በአላህ በጎ ፈቃድ ብቻ መሆኑን፤
10. በእምነት መከፋፈል የመጨረሻ ውጤቱ እጅግ የከፋ እንደሆነ፤
11. ለአላህ ዲን (ሃይማኖት) ሲባል ገንዘብን አውጥቶ መስጠት በአላህ ዘንድ ከፍ ያለ ክብርንና ምንዳን እንደሚያስገኝ፤
12. ከአላህ በስተቀር ማንም የአምላክነት ስልጣን እንደሌለው፤
13. ከአላህ ባህሪያቶች በጥቂቱ ማውሳት፤
14. ሽምግልና በአላህ ፍቃድ ብቻ እንደሚሆን መግለፅ፤
15. ሰዎች አላህ ካሳወቃቸው በስተቀር ስውር ነገሮችን ማንም ሊያውቃቸው እንደማይችል፤
16. አላህ ኩርሲ እንዳለውና ኩርሲዉም ሰማይንና ምድሩን እንደሚበልጥ፤
17. የመፅሐፍ ባለቤቶች፤ መጁሳና ሳቢያኖች በ አስተዳደር ስር ሲኖሩ ሃይማኖታቸውን ለቀው ወደ ኢስላም እንዲገቡ ጥሪ ይደረግላቸዋል እምቢ ቢሉም ጂዚያ (ግብር) እየከፈሉ በሰላም እንዲኖሩ እንደሚገደዱ፤

18. ቀናው መንገድ ማለት የኢስላም ሃይማኖት ብቻ እንደሆነና ሌላው ሃይማኖት ተብዬ ሁሉ ባጢል መሆኑን፤
19. ፅዳትን መጠበቅ በጌጣጌጥ ከማሸብረቅ ቅድሚያ እንደሚሰጠው፤
20. የላኢላሀ ኢለሏህ ትርጓሜ አምልኮን ለአንድ አላህ ብቻ ማድረግና ከእርሱ ውጭ የሆነ ጣኦታትን በሙሉ መካድ መሆኑን፤
21. የአላህን ወዳጅነት ማግኘት የሚቻለው በትክክለኛ እምነት መሆኑን፤
22. አላህ ምን ጊዜም ወዳጆቹን እንደሚንከባከብና ከርሱ ወዳጅነት የራቁት ግን ድልን እንደማያገኙ፤
23. ስለዚህ ሰው ማንነት በቁርጥ መግለፅ ባይቻልም ኑምሩድ ወይም ሐሙራቢ ሊሆን ይችላል የሚሉት ብዙ ናቸው።
24. እምነት በልባቸው ሰርፆ ያልገባ የአላህ ፀጋ ሲፈስባቸው አላህን ከማመስገን ይልቅ የበለጠ በኩራት እንደሚንጠባረሩ፤
25. አላህ ለአገልጋይ ባሪያዎቹ ድልን ያጎናፅፋቸዋል። ህሊናቸውንም የሚያረጋጋ ማስረጃ እንደሚሰጣቸው።
26. ግፍን ያለ ምንም ይሉኝታ የሚያራምድ ሰው አላህ ወደ መልካም መንገድ የሚያስገባውን ሂደት እንደሚነፍገው፤
27. ትክክለኛውን እምነት ለሰዎች ለማስረዳት ክርክር ማካሄድ የተፈቀደ መሆኑን፤
28. ሰው በትክክል ሊያሳምነው የሚችል ነገር እስከሚከሰት ድረስም ካጠራጠሩት ጉዳዮች ራሱን ማግለል እንደሚገባው፤
29. የአላህ ሀይል እጅግ የገዘፈና የከበደ መሆኑን፤
30. ከሞት በኋላ ዳግም ሕይወት እንዳለና ሰው ሙቶ እንደማይቀር ማመን እንደሚገባ፤
31. አላህ ለትክክለኛ አማኞች እጅግ የቀረበ ድጋፉም የማይቋረጥና ቀጣይነት ያለው ስለ መሆኑ እንማራለን።

وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِـۧمُ رَبِّ أَرِنِى كَيْفَ تُحْىِ ٱلْمَوْتَىٰ ۖ قَالَ أَوَلَمْ تُؤْمِن ۖ قَالَ بَلَىٰ وَلَـٰكِن لِّيَطْمَئِنَّ قَلْبِى ۖ قَالَ فَخُذْ أَرْبَعَةً مِّنَ ٱلطَّيْرِ فَصُرْهُنَّ إِلَيْكَ ثُمَّ ٱجْعَلْ عَلَىٰ كُلِّ جَبَلٍ مِّنْهُنَّ جُزْءًا ثُمَّ ٱدْعُهُنَّ يَأْتِينَكَ سَعْيًا ۚ وَٱعْلَمْ أَنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٢٦٠﴾

**260.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂም «ጌታዬ ሆይ! ሙታንን እንዴት ሕያው እንደምታደርግ እስቲ አሳየኝ ባለ ጊዜ (የሆነውን ታሪክ አስታውስ)። አላህ፡- አላመንክምን?» አለው። ኢብራሂም በፍፁም (አይደለም) አምኛለሁ። ግን ልቤ ሙሉ በሙሉ እንዲረጋጋ ነው አለው። አላህም፡- አራት ወፎችን ያዝና ወደ አንተ ሰብስባቸው። ከዚያ ቆራርጣቸው። ከዚያም በየኮረብታው ሁሉ ላይ ከእነርሱ ቁራጭ ቁራጭ አካላቸውን አስቀምጥ። ከዚያም ጥራቸው በፍጥነት ወደ አንተ ይመጣሉ። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ መሆኑን እወቅ አለው።

مَّثَلُ ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ أَمْوَٰلَهُمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ كَمَثَلِ حَبَّةٍ أَنۢبَتَتْ سَبْعَ سَنَابِلَ فِى كُلِّ سُنۢبُلَةٍ
مِّاْئَةُ حَبَّةٍ ۗ وَٱللَّهُ يُضَٰعِفُ لِمَن يَشَآءُ ۗ وَٱللَّهُ وَٰسِعٌ عَلِيمٌ ﴿٢٦١﴾ ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ أَمْوَٰلَهُمْ فِى سَبِيلِ
ٱللَّهِ ثُمَّ لَا يُتْبِعُونَ مَآ أَنفَقُوا۟ مَنًّا وَلَآ أَذًى ۙ لَّهُمْ أَجْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا
هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿٢٦٢﴾ ۞ قَوْلٌ مَّعْرُوفٌ وَمَغْفِرَةٌ خَيْرٌ مِّن صَدَقَةٍ يَتْبَعُهَآ أَذًى ۗ وَٱللَّهُ غَنِىٌّ حَلِيمٌ ﴿٢٦٣﴾

**261-263.** እነዚያ ገንዘቦቻቸውን በአላህ መንገድ የሚለግሱ ሰዎች ልግስና ምሳሌ በየዘለላው ሁሉ መቶ ቅንጣት ያለባቸውን ሰባት ዘለላዎች እንዳበቀለች አንዲት ቅንጣት ምሳሌ ነው። አላህ ለሚሻው ሰው ሁሉ ከዚህ በላይ አባዝቶ ይለግሳል። አላህ ችሮታው ሰፊና ዐዋቂ ነውና። እነዚያ ገንዘቦቻቸውን በአላህ መንገድ የሚለግሱ ከዚያ በሰጡት ነገር መመፃደቅና ማስከፋት የማያስከትሉ ሰዎች ሁሉ ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አለላቸው። በእነርሱም ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው አያዝኑም። መልካም ንግግርና ይቅር ባይነት ብቻ ማስከፋት ከሚከተለው ምፅዋት በላጭ ነው። አላህ በራሱ ተብቃቂና ታጋሽ ነውና።

ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (245-261) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አልበቀረህ አንቀፅ (261) ኛው በወረደ ጊዜ ነብዩ (ﷺ) የኡመቶቸን ምንዳ እጥፍ ድርብ አድርግልኝ ብለው ዱዓ ስላደረጉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

ከላሚ ምዕራፍ አንቀፅ (262) የወረደበት ምክንያት፡- ዑሥማን ኢብኑ ዐፋንና ዐብዱረሕማን ኢብኑ ዐውፍ በተባሉ ሀብታም ሙስሊሞች (ሶሃቦች) ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ምክንያቱም አብድረህማን ብኑ ዐውፍ አራት ሺህ ዲርሃም ወደ ነብዩ ይዞ መጥቶ ንብረቴ ስምንት ሺህ ዲርሃም ሲሆን አራቱን ለእኔና ለቤተሰቤ አስቀርቼ አራቱን ለጌታ አበድሬዋለሁ ሲል ነብዩ በሰጠኸውና ባስቀረኸውም አላህ ይባርክልህ ብለውት ነበር። ኡስማን ኢብኑ ዐፋንም በተቡክ ዘመቻ አንድ ሺህ ግመሎችን ከነቅጠልና ስንቃቸው ከመቻሉም አልፎ የሩማህ የውሃ ጉድጓድ ለሙስሊሞች አገልግሎት እንድትውል ሰጡ። በተጨማሪም መጓጓዣና ስንቅ ለሌለው ሁሉ እኔ አለሁኝ በማለቱ ነብዩ የኡስማንን እጅ ይዘው ጌታዬ ሆይ! ኡስማንን ወድጄለታለሁና ውደድለት ሰዎች ሆይ! ኡስማን ከዚህ በኋላ ያደረገውን ቢያደርግ ምንም የለበትም ባሉ ጊዜ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تُبْطِلُوا۟ صَدَقَـٰتِكُم بِٱلْمَنِّ وَٱلْأَذَىٰ كَٱلَّذِى يُنفِقُ مَالَهُۥ رِئَآءَ
ٱلنَّاسِ وَلَا يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ ۖ فَمَثَلُهُۥ كَمَثَلِ صَفْوَانٍ عَلَيْهِ تُرَابٌ فَأَصَابَهُۥ وَابِلٌ
فَتَرَكَهُۥ صَلْدًا ۖ لَّا يَقْدِرُونَ عَلَىٰ شَىْءٍ مِّمَّا كَسَبُوا۟ ۗ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْكَـٰفِرِينَ ﴿٢٦٤﴾
وَمَثَلُ ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ أَمْوَٰلَهُمُ ٱبْتِغَآءَ مَرْضَاتِ ٱللَّهِ وَتَثْبِيتًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ كَمَثَلِ جَنَّةٍۭ
بِرَبْوَةٍ أَصَابَهَا وَابِلٌ فَـَٔاتَتْ أُكُلَهَا ضِعْفَيْنِ فَإِن لَّمْ يُصِبْهَا وَابِلٌ فَطَلٌّ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ

بَصِيرٌ ﴿٢٦٥﴾ أَيَوَدُّ أَحَدُكُمْ أَن تَكُونَ لَهُۥ جَنَّةٌ مِّن نَّخِيلٍ وَأَعْنَابٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ
لَهُۥ فِيهَا مِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ وَأَصَابَهُ ٱلْكِبَرُ وَلَهُۥ ذُرِّيَّةٌ ضُعَفَآءُ فَأَصَابَهَآ إِعْصَارٌ فِيهِ نَارٌ
فَٱحْتَرَقَتْ ۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمُ ٱلْءَايَٰتِ لَعَلَّكُمْ تَتَفَكَّرُونَ ﴿٢٦٦﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟
أَنفِقُوا۟ مِن طَيِّبَٰتِ مَا كَسَبْتُمْ وَمِمَّآ أَخْرَجْنَا لَكُم مِّنَ ٱلْأَرْضِ ۖ وَلَا تَيَمَّمُوا۟ ٱلْخَبِيثَ مِنْهُ
تُنفِقُونَ وَلَسْتُم بِـَٔاخِذِيهِ إِلَّآ أَن تُغْمِضُوا۟ فِيهِ ۚ وَٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ غَنِىٌّ حَمِيدٌ ﴿٢٦٧﴾

**264-267.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! እንደነዚያ ገንዘብን ለሰዎች ለማሳየት ሲል እንደሚሰጠውና በአላህና በመጨረሻው ቀን እንደማያምነው ሰው መፅዋቶቻችሁን በመመፃደቅና ተረጂውን በማስከፋት አታበላሹ። (የዚህ አይነቱም ድርጊት) ምሳሌው በላዩ ላይ አፈር እንዳለበት ለስላሳ ድንጋይ ሲሆን እሱም ሀይለኛ ዝናብ እንዳገኘውና እንደተራቆተ ብጤ ነው። እኒህ አይነት ሰዎች ከሰሩት ነገር በምኑም ሊጠቀሙ አይችሉም። አላህ ከሓዲያን ሕዝቦችን በፍፁም ወደ ቀናው መንገድ አይመራምና። የእነዚያ የአላህን ውዴታ ለመፈለግና ከነፍሶቻቸው (እምነትን) ለማረጋገጥ ብለው ገንዘቦቻቸውን የሚለግሱ ሰዎች ሁሉ ምሳሌ በተስተካከለች ከፍተኛ ቦታ ላይ ባለች አትክልት ሲሆን ይህች አትክልት ከፍተኛ ዝናብ አግኝታ እጥፍ ድርብ ምርት እንደሰጠች ከፍተኛ ዝናብ ባታገኝ እንኳን ካፊያ ብቻ እንደሚበቃት የአትክልት አይነት ይመስላል። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና። ከናንተ አንዳችሁ ሁሉን ዓይነት ምርት የምትሰጥ የዘንባባዎችና የወይኖች የአትክልት ቦታ ልትኖረው እርጅናም ሊነካውና በእነርሱም ረዳት የለሽ ህፃናት ያሉት ሲሆኑ በውስጡ እሳት ያለበት ውርጭ ምርቱ ላይ አደጋ ሊደርስበት እና ልትቃጠል ይወዳልን? ልክ እንደዚሁ አላህ አንቀፆችን ለእናንተ ያብራራል። ልታስተነትኑት* ይከጀላልና። እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከአፈራችሁትና ከዚያ ለእናንተ ከምድር ካወጣንላችሁ ከመልካሙ ለግሱ። መጥፎውንም ለመስጠት አታስቡ። እርሱን ለራሳችሁ አይኖቻችሁን ጨፍናችሁ እንጂ የማትወስዱት ስትሆኑ ከእርሱ ከመጥፎ ትሰጣላችሁን? አላህ ተብቃቂና ምስጉን መሆኑን እወቁ።

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዑመር እንዲህ ብለዋል፡- «ይህን የአላህን ትዕዛዝ በማክበር መልካም ስራዎችን የሚፈፅም ሰው ምሳሌ ነው። አላህ ወደዚህ ሰው ሸይጣንን ይልክና የሰራቸው መልካም ሥራዎች እስኪጠፉ ድረስ ኃጢአቶችን እንዲፈፅም ያደርገዋል»

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (260-264) ከምናገናቸው አንኳር ነጥቦች፡-**

1. የሰው ልጅ ያላወቃቸው አዲስ ነገሮች ለማወቅ ጥብቅ ፍላጎትና ጉጉት እንዳለው፤
2. አላህ ለነብዩ ኢብራሂም የተለየ ውዴታ እንደነበረውና እንክባካቤውና እርዳታውን ይለግሳቸው እንደነበር፤
3. ሰው የአላህን ጥበብና በፍጡራት ላይ የሚንፀባረቀው የእሱ ተዐምር በተመለከተ ቁጥር ማንነቱ ሊጨምር እንደሚችል፤
4. ለጂሃድ ለታቀደው ጦርነት ማካሄጃ የሚውል ገንዘብ ማውጣት ከፍተኛ ምንዳ እንደሚያስገኝ፤
5. ሰደቃ አጅሩ እጅግ የበዛ ለመንፈስ የሚሰጠው ደስታና እርካታ ደግሞ እንደዚያው ጥልቅ መሆኑን፤
6. ሰደቃ ከሰጠን በኋላ መመፃደቅ እጅግ የተከለከለ ነውረኛ ተግባር መሆኑን፤
7. የመስጠት አቅም የሌለው ጠያቂውን በመልካም ፊት ተቀብሎ በጥሩ አንደበት መልካሙን ተመኝቶ መሸኘት እንደሚገባ፤
8. ለመመፃደቅና ለጉራ ሰደቃ መስጠት ምንም አይነት አኼራዊ ፋይዳ እንዳማያስገኝ እንማራለን።

ከላሚ ምዕራፍ (267) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የፊጥር ዘካ በተደነገገበት ጊዜ አንድ ሰውዬ መናኛና ያልተቀሸረ ተምር ይዞ መጥቶ ለነበዩ ሲሰጥ ነው ይህ አንቀፅ የወረደ። (ዋሒዲ፤ ሓኪም እና ዘሀቢ)

ٱلشَّيۡطَٰنُ يَعِدُكُمُ ٱلۡفَقۡرَ وَيَأۡمُرُكُم بِٱلۡفَحۡشَآءِۖ
وَٱللَّهُ يَعِدُكُم مَّغۡفِرَةٗ مِّنۡهُ وَفَضۡلٗاۗ وَٱللَّهُ وَٰسِعٌ عَلِيمٞ ٢٦٨

**268.** ሰይጣን እንዳትለግሱ በድህነት ያስፈራራችኋል። በመጥፎም ያዛችኋል። አላህ ከእርሱ የሆነን ምህረትና ችሮታን ሊያጎናፅፋችሁ ተስፋ ሰጥቷችኋል። አላህ ችሮታው ሰፊና ሁሉን ዐዋቂ ነው።

يُؤۡتِي ٱلۡحِكۡمَةَ مَن يَشَآءُۚ وَمَن يُؤۡتَ ٱلۡحِكۡمَةَ فَقَدۡ أُوتِيَ خَيۡرٗا كَثِيرٗاۗ
وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّآ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٢٦٩

**269.** አላህ ለሚሻው ሰው ጥበብን ይሰጣል። ጥበብንም የሚስ-ሰጥ ሰው ሁሉ ብዙ መልካም ነገርን በእርግጥ ተሰጥቷል። የአዕምሮ ባለቤቶች እንጂ ሌላው አይገሰፅም።

**ከላሚ ምዕራፍ ከአንቀፅ (265-269) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፡-**

1. ከማስተማሪያ ዘዴዎች አንዱ በምሳሌ እያጣቀሱ ማስረዳት በመሆኑ ይህንን ዘዴ መጠቀም አስፈላጊ እንደሆነ፤
2. ከይዩልኝ፤ ከይስሙልኝና ከመመፃደቅ የጠራ ንፁህ ሰደቃ የሚያስገኘው ምንዳ በብዙ እጥፍ ተባዝቶ ሲሆን፤ ለይዩልኝ የተሰጠ ደግሞ ፋይዳ ቢስ እንደሆነ፤

3. የአላህ ተዐምራቶች እያስተነተኑ የእርሱን ታላቅነት በሚገልፁ ነገሮች ዙሪያ መመራመር ግዴታ ስለመሆኑ፤
4. በወርቅ፤ በብር፤ ከእንስሳት ሀብቶች መጠናቸው የዘካ ማውጫ እርከን ላይ ከደረሰ ዘካ ማውጣት ግዴታ መሆኑን፤
5. ከመሬት ከሚበቅሉ አዝዕርቶችና ከከርሰ ምድር ከሚገኙ ማዕዳናት ዘካን መክፈል ግዴታ ስለ መሆኑ፤
6. በዘካ አወጣጥ ወቅትም ሆነ በትርፍ ሰደቃ ስጦታ ወቅት መጥፎውን መርጦ መስጠት አስቀያሚ ተግባር መሆኑን፤
7. ሰይጣን ግልፅና አሳሳች ጠላታችን በመሆኑ እርሱን መታገልና መዋጋት ተገቢ መሆኑን፤
8. ከገንዘብ ቁሳዊ ንብረት ይልቅ እውቀት ከፍተኛ ብልጫ እንዳለው እንማራለን።

وَمَآ أَنفَقْتُم مِّن نَّفَقَةٍ أَوْ نَذَرْتُم مِّن نَّذْرٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُهُۥ ۗ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٢٧٠﴾

**270.** ከምፅዋት ማንኛውንም የለገሳችሁትን ወይም ከስለት የተሳላችሁትን አላህ ጠንቅቆ ያውቀዋል። ለበዳዮች (ግፈኞች) ሁሉ ምንም አይነት ረዳቶች የሏቸውም።

إِن تُبْدُوا۟ ٱلصَّدَقَٰتِ فَنِعِمَّا هِىَ ۖ وَإِن تُخْفُوهَا وَتُؤْتُوهَا ٱلْفُقَرَآءَ فَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۚ
وَيُكَفِّرُ عَنكُم مِّن سَيِّـَٔاتِكُمْ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ﴿٢٧١﴾

**271.** ምፅዋቶችን ብትገልፁ እርሷ ምንኛ መልካም ተግባር ናት። ብትደብቋትና ለድሆች ብትሰጧት እርሱ ለእናንተ በላጭ ነው። ከኃጢአቶቻችሁ ከናንተ ያብሳል። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና።

ከላሚ ምዕራፍ (271) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሶሃቦች በየላሚ ምዕራፍበ (215) ላይ ያለው የቁርአን አንቀፅ በወረደ ጊዜ በሚስጢር መሰደቅ ይሻላል ወይስ በይፋ መሰደቅ ብለው ነብዩን (ﷺ) ስለጠየቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ፤ እና ኢብኑ ከሲር)

۞ لَّيْسَ عَلَيْكَ هُدَىٰهُمْ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَهْدِى مَن يَشَآءُ ۗ وَمَا تُنفِقُوا۟ مِنْ خَيْرٍ فَلِأَنفُسِكُمْ ۚ
وَمَا تُنفِقُونَ إِلَّا ٱبْتِغَآءَ وَجْهِ ٱللَّهِ ۚ وَمَا تُنفِقُوا۟ مِنْ خَيْرٍ يُوَفَّ إِلَيْكُمْ وَأَنتُمْ لَا تُظْلَمُونَ ﴿٢٧٢﴾

**272.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱን ማቅናት በአንተ ላይ ግዴታ የለብህም። አላህ ግን የሚሻውን ሰው ያቀናል። የምትለግሱት ገንዘብ ሁሉ ምንዳው ለነፍሶቻችሁ ብቻ ነው። የአላህን ውዴታውን በመፈለግ እንጂ ምንም አትለግሱ። ከገንዘብም የምትለግሱት ሁሉ ምንዳው ወደ እናንተ ይሞላል። እናንተም ቅንጣት ያህል አትበደሉም።

ከላሚ ምዕራፍ (272) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙስሊሞች ለከሃዲ ዘመዶቻቸው የትኛውንም የስጦታ አይነት መስጠት ይከብዳቸው ስለ ነበር ለማንም ችግረኛ መስጠት ምንም ችግር እንደሌለው ለማስተማር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ፤ ኢብኑ ከሲር፤ ቁርጡቢ፤ ዛዱል መሲር)

لِلْفُقَرَآءِ ٱلَّذِينَ أُحْصِرُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ لَا يَسْتَطِيعُونَ ضَرْبًا فِى ٱلْأَرْضِ يَحْسَبُهُمُ ٱلْجَاهِلُ أَغْنِيَآءَ مِنَ ٱلتَّعَفُّفِ تَعْرِفُهُم بِسِيمَٰهُمْ لَا يَسْـَٔلُونَ ٱلنَّاسَ إِلْحَافًا ۗ وَمَا تُنفِقُوا۟ مِنْ خَيْرٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٌ ﴿٢٧٣﴾

**273.** ምፅዋት የምትሰጡተ ዘካና ልገሳ ለእነዚያ በአላህ መንገድ በግል ሕይወታቸው ከመንቀሳቀስ (ለታገዱት) ፋታ ላጡ ድሆች ነው። በምድር መሄድን አይችሉም። ከቁጥብነታቸው የተነሳ ውስጣቸውን የማያውቅ ሰው ሁሉ ሀብታሞች ናቸው ብሎ ያስባቸዋል (ይገምታቸዋል)። በምልክታቸው ታውቃቸዋለህ። ሰዎችን በችክታ አይለምኑም። ከገንዘብም የምትለግሱትን ሁሉ አላህ እርሱ አዋቂ ነው።

ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ أَمْوَٰلَهُم بِٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ سِرًّا وَعَلَانِيَةً فَلَهُمْ أَجْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ وَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿٢٧٤﴾

**274.** እነዚያ ገንዘቦቻቸውን በሌሊትና በቀን በድብቅም ሆነ በግልፅ የሚለግሱ ሰዎች ሁሉ ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ ዋጋቸው ይስ-ሰጣቸዋል። በእነርሱም ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው* አያዝኑም።

* በተመሳሳይ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሰባት ሰዎችን አላህ በዚያ ፀሐይ ተቃርባ ጥላ በማይኖርበት በትንሳኤ ቀን በአርሹ ጥላ ስር ያደርጋቸዋል። እነሱም፡-

1. ፍትሃዊ መሪ፤
2. አላህን በመገዛት ተግባር ላይ ያደገ ወጣት፤
3. ልቡናው ወደ መስጂድ ዘወትር የተንጠለጠለ ሰው፤
4. ለአላህ ሲሉ የተዋደዱትና በዚያው ላይም የተለያዩ ሁለት ሰዎች፤
5. አንዲት ውብና ቆንጆ የሆነች ሴት ሕጋዊ ያልሆነ ወሲባዊ ግንኙነት ዝሙት ከእሷ ጋር እንዲፈፅም ስትጠራው፤ «እኔ አላህን እፈራለሁ» በማለት ግብዣዋን እምቢኝ ያለ ሰው፤
6. ቀኝ እጁ ምፅዋት በሚሰጥበት ወቅት ግራ እጁ በማያይበት አኳኋን ምፅዋትን በድብቅ የሚሰጥ፤
7. አላህን ለብቻው የሚያመልክና አይኖቹ በእንባ የሚታጠቡ የሆነ ሰው።»

ከላሚ ምዕራፍ (274) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ይህ አንቀፅ ለአላህ ዲን ብለው በፈረሶቻቸው ላይ ሆነው ዘብ የሚቆሙትን ሙጃሂዶች ለማሞገስ የወረደ አንቀፅ ነው ብለዋል። (ዋሒዲ)

**ከላሟ ምዕራፍ አንቀፅ (270-274) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፦**

1. የሰደቃ መጠኑ የሚያስገኘውን ምንዳ እንደማያስቀረውና በንፁህ ልብ ንያ ትንሽም ሰደቃ ብዙ የሆነ ምንዳ ከአላህ ያሰጣል። ለይዩልኝና ይስሙልኝ የሚጋብዝ ሁኔታ ካልተፈራ ወይም ለጉራ ታስቦ ካልሆነ በስተቀር ሰደቃን በይፋ መስጠቱ ሌላውን ክፍልም እንደሚያነሳሳ ከታሰበ ተገቢ ነው። ሆኖም በሚስጥር የሚሰጥ ሰደቃ ደግሞ የበለጠ ምንዳ ያስገኛል።
2. ከዘካ በስተቀር ማንኛውም አይነት ሰደቃ ሙስሊም ላልሆኑ ሰዎችም መስጠት የሚቻል መሆኑን፤
3. በሰደቃ ሂደት በይበልጥ ተጠቃሚ ክፍል ተቀባይ ሳይሆን ሰጪው ክፍል መሆኑን፤
4. በሰደቃ አሰጣጥ ጊዜ ሰጪው ሰው ስጦታውን በሙሉ ልብ ለአላህ ብሎ መስጠቱ አስፋላጊ እንደሆነ፤
5. ሰደቃ የሚሰጣቸው ሰዎች የችግር መጠንና የችግር አይነት እንደተቀባዩቹ ችግር የተለያየ አጅሩም የሚበልጥ መሆኑን፤
6. ችግርን ተቋቁሞ ሰውን ምፅዋት ከመጠየቅ ራስን መቆጠብ በአላህ ዘንድ ክብር እንደሚያሰጥና ክብር እንደሚያጎናፅፍ፤
7. ሰደቃ ለመስጠት የጊዜ ምርጫ ሳይገድበው በሌሊትም ሆነ በቀን በይፋም ሆነ በድብቅ መስጠት እንደሚቻል እንማራለን።

ٱلَّذِينَ يَأْكُلُونَ ٱلرِّبَوٰاْ لَا يَقُومُونَ إِلَّا كَمَا يَقُومُ ٱلَّذِى يَتَخَبَّطُهُ ٱلشَّيْطَٰنُ مِنَ ٱلْمَسِّ ۚ
ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَالُوٓاْ إِنَّمَا ٱلْبَيْعُ مِثْلُ ٱلرِّبَوٰاْ ۗ وَأَحَلَّ ٱللَّهُ ٱلْبَيْعَ وَحَرَّمَ ٱلرِّبَوٰاْ ۚ فَمَن جَآءَهُۥ
مَوْعِظَةٌ مِّن رَّبِّهِۦ فَٱنتَهَىٰ فَلَهُۥ مَا سَلَفَ وَأَمْرُهُۥٓ إِلَى ٱللَّهِ ۖ وَمَنْ عَادَ فَأُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ
ٱلنَّارِ ۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٢٧٥﴾

**275.** እነዚያ አራጣን የሚበሉ ሁሉ ያ ሰይጣን ሰፍኖበት ራሱን የሚስት ሰው ከአውድቅቱ እንደሚነሳ አይነት ሁነው እንጂ (ከመቃብራቸው) አይነሱም። ይህም የሆነው እነርሱ መሸጥ ልክ እንደ አራጣ ነው በማለታቸው ነው። አላህ ግን መሸጥን ፈቅዷል። አራጣን እርም አድርጓል። ከጌታው ግሳጼ የመጣለት እና ከዚያ የተከለከለ ሰው ሁሉ ከዚህ አዋጅ በፊት ያካበተውን እንደያዘ መቆየት ይችላል። የወደፊት እጣፈንታው ወደ አላህ ነው። አራጣን ወደ መብላት የተመለሱ ሰዎች እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘወታሪዎች ናቸው።

يَمْحَقُ ٱللَّهُ ٱلرِّبَوٰاْ وَيُرْبِى ٱلصَّدَقَٰتِ ۗ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ كُلَّ كَفَّارٍ أَثِيمٍ ﴿٢٧٦﴾

**276.** አላህ የአራጣን ገንዘብ ያከስማል (በረከቱን ያጠፋል)። መልካም ልገሳዎችን ያፋፋል። አላህም ኃጢአተኛንና ከሓዲን ሁሉ አይወድምና።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَوُاْ ٱلزَّكَوٰةَ لَهُمۡ أَجۡرُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ وَلَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ﴿٢٧٧﴾

277. እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑ ሰዎች መልካም ስራዎችንም የሰሩ፣ ሶላትን አስተካክለው የሰገዱና ዘካንም የሰጡ እነርሱ በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው አላቸው፤ በእነርሱም ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው አያዝኑምም።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَذَرُواْ مَا بَقِيَ مِنَ ٱلرِّبَوٰٓاْ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ﴿٢٧٨﴾

278. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ። በእንጥልጥል ላይ ያሉ (ያልተሰበሰቡ) የወለድ ክፍያዎችን አትውሰዱ። ትክክለኛ አማኞች ከሆናችሁ (ተጠንቀቁ)።

ከላሟ ምዕራፍ (278) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) በሰባተኛ ዓመት ሂጅራ ላይ ባደረጉት ዑምራ አስማእ ቢንት አቡበክር አብራቸው ነበረችና በዚህ ጊዜ ያልሰለሙት እናቷ ቁተየሏህ እና አያቷ እርዳታ ስለጠየቋት ኢስላምን ካልተቀበላችሁ በእናንተ ጉዳይ ነብዩን ሳልጠይቅ ምንም አልሰጣችሁም። ስላለች ወደ ነብዩ በመሄድ ስለጠየቀቻቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። በኒ ዐምር እና በኒ ሙጊራ የተባሉ ብሔሮች ለሰቂፍ ብሔሮች በወለድ ብር ይሰጡ ነበር። ነብዩ (ﷺ) መካን ተቆጣጥረው ከዕብ ኢብኑ ኡሰይድን ባስተዳዳሪነት ከሾሙ በኋላ ወለድ የተባለን አውግዘው ወደ መዲና ተመለሱ። በዚህም ጊዜ እነዚህ ሰዎች ወደ ከዕብ በመምጣት ምነው በወለድ እርጉሞች ሆነን ከእኛ ሌላ ባሉ ሰዎች ወለድ ተወገዘ ሲሉ ከዕብ ይህንን ጉዳይ ለረሱል በመላኩ እነዚህ አያቶች ወረዱ። በዚህ ጊዜም በአላህና ከነብዩ (ﷺ) ጋር ጦርነት እንደማይችሉ ተረዱ። (ዋሒዲ)።

فَإِن لَّمۡ تَفۡعَلُواْ فَأۡذَنُواْ بِحَرۡبٖ مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۖ وَإِن تُبۡتُمۡ فَلَكُمۡ رُءُوسُ أَمۡوَٰلِكُمۡ لَا تَظۡلِمُونَ وَلَا تُظۡلَمُونَ ﴿٢٧٩﴾

279. የታዘዛችሁትን ባትሰሩ ከአላህና ከመልዕክተኛ ጦርነት ታውጀባችኋል። ከወለዳዊ ድርጊታችሁ ብትታቀቡ ግን አንጡራ ገንዘባችሁ ለእናንተው እንደተጠበቀ ነው። እናንተም አትበደሉም ሌሎችንም አትበድሉምም።

وَإِن كَانَ ذُو عُسۡرَةٖ فَنَظِرَةٌ إِلَىٰ مَيۡسَرَةٖۚ وَأَن تَصَدَّقُواْ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ﴿٢٨٠﴾

280. የድህነት ባለቤት ባለዕዳ ሰው ቢኖር ገንዘብ እስኪያገኝ ድረስ ማቆየት ነው። (የእፎይታ ጊዜ ይሰጠው) ስጡት። እዳውን በበጎ አድራጊነት ሙሉ በሙሉ ብትሰርዙለት ለእናንተ በላጭ ነው የምታውቁ ብትሆኑ (ትሰሩታላችሁ)።

ከላሟ ምዕራፍ (280) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ በኒ አምር የተባሉ ለበኒ ሙጊራዎች በወለድ አበድረዋቸው ነበር።«ዋና ገንዘባችንን ስጡንና ወለዱ ይቅርላችሁ» ይሏቸዋል። በኒ ሙጊራዎች ግን «እኛ ዛሬ በችግር ላይ ነንና አዝመራ እስከሚደርስ ቆዩልን» አሏቸው። አበዳሪዎቹ የበኒ-አምር ሰዎች ግን እንቢ አሉ። በዚህ ሰበብ ነው ይህ የቁርኣን አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ ለሰዎች ገንዘብ የሚያበድር ሰው ነበር። ይህ ሰው ለአገልጋዩ «የተቸገረ ሰው ስታገኝ እለፈው ምናልባት አላህ ወንጀሎቻችንን ያልፍልናልና ይለው ነበር። ከሞተ በኋላ አላህን አገኘና ወንጀሎቹን ይቅር አለለት»

وَٱتَّقُواْ يَوۡمٗا تُرۡجَعُونَ فِيهِ إِلَى ٱللَّهِۖ ثُمَّ تُوَفَّىٰ كُلُّ نَفۡسٖ مَّا كَسَبَتۡ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ ﴿٢٨١﴾

**281.** ያን በርሱም ውስጥ ወደ አላህ የምትመለሱበትን ቀን ፍሩ። ሁሉም ነፍስ ያኔ ከሰራችው አኳያ ዋጋዋን ታገኛለች። በዚያ ዕለት (በሱ ዉስጥ) ተበዳይ ወገኖች አይኖሩም።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (275-281) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፦**

1. ወለድ አስከፊ ማህበራዊና ሃይማኖታዊ ወንጀል መሆኑን፤
2. ያለምንም ይሉኝታ አራጣን እየበላ የሚኖርን ሙስሊም የሙስሊም መሪዎች ከዚህ ተግባሩ ሊያስቆሙት እንደሚገባ፤
3. በወለድ ተግባርም ሆነ በሌሎች ኃጢአቶች የተዘፈቀ ሰው ቶሎ ከወንጀሉ ተመልሶ ንስሀ መግባት እንዳለበት፤
4. ከአራጣ ተግባር ተፀፅቶ የተመለሰ ሰው የራሱ የነበረው ዋናው ገንዘቡ የራሱ ሀብት እንደሆነ ታውቆ እንደማይነካበት፤
5. የአኼራን ህይወት ማስታወስና ለእሷ መዘጋጀት በሙስሊሞች ላይ የተጣለ ግዴታ መሆኑን እንማራለን።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا تَدَايَنتُم بِدَيۡنٍ إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمّٗى فَٱكۡتُبُوهُۚ وَلۡيَكۡتُب بَّيۡنَكُمۡ كَاتِبُۢ
بِٱلۡعَدۡلِۚ وَلَا يَأۡبَ كَاتِبٌ أَن يَكۡتُبَ كَمَا عَلَّمَهُ ٱللَّهُۚ فَلۡيَكۡتُبۡ وَلۡيُمۡلِلِ ٱلَّذِي عَلَيۡهِ ٱلۡحَقُّ
وَلۡيَتَّقِ ٱللَّهَ رَبَّهُۥ وَلَا يَبۡخَسۡ مِنۡهُ شَيۡـٔٗاۚ فَإِن كَانَ ٱلَّذِي عَلَيۡهِ ٱلۡحَقُّ سَفِيهًا أَوۡ ضَعِيفًا
أَوۡ لَا يَسۡتَطِيعُ أَن يُمِلَّ هُوَ فَلۡيُمۡلِلۡ وَلِيُّهُۥ بِٱلۡعَدۡلِۚ وَٱسۡتَشۡهِدُواْ شَهِيدَيۡنِ مِن رِّجَالِكُمۡۖ
فَإِن لَّمۡ يَكُونَا رَجُلَيۡنِ فَرَجُلٞ وَٱمۡرَأَتَانِ مِمَّن تَرۡضَوۡنَ مِنَ ٱلشُّهَدَآءِ أَن تَضِلَّ إِحۡدَىٰهُمَا
فَتُذَكِّرَ إِحۡدَىٰهُمَا ٱلۡأُخۡرَىٰۚ وَلَا يَأۡبَ ٱلشُّهَدَآءُ إِذَا مَا دُعُواْۚ وَلَا تَسۡـَٔمُوٓاْ أَن تَكۡتُبُوهُ صَغِيرًا
أَوۡ كَبِيرًا إِلَىٰٓ أَجَلِهِۦۚ ذَٰلِكُمۡ أَقۡسَطُ عِندَ ٱللَّهِ وَأَقۡوَمُ لِلشَّهَٰدَةِ وَأَدۡنَىٰٓ أَلَّا تَرۡتَابُوٓاْ إِلَّآ أَن
تَكُونَ تِجَٰرَةً حَاضِرَةٗ تُدِيرُونَهَا بَيۡنَكُمۡ فَلَيۡسَ عَلَيۡكُمۡ جُنَاحٌ أَلَّا تَكۡتُبُوهَاۗ
وَأَشۡهِدُوٓاْ إِذَا تَبَايَعۡتُمۡۚ وَلَا يُضَآرَّ كَاتِبٞ وَلَا شَهِيدٞۚ وَإِن تَفۡعَلُواْ فَإِنَّهُۥ فُسُوقُۢ بِكُمۡۗ وَٱتَّقُواْ
ٱللَّهَۖ وَيُعَلِّمُكُمُ ٱللَّهُۗ وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ ﴿٢٨٢﴾

**282.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ በእዳ በተዋዋላችሁ ጊዜ ፃፉት። ፀሐፊዉም በመካከላችሁ በትክክል ይፃፍ። ፀሐፊም አላህ እንዳሳወቀው መፃፍን ለመፃፍ እንቢ አይበል። ይፃፍም። ያም በእርሱ ላይ እዳው ያለበት ሰው በቃሉ ያለበትን ያስፅፍ። ጌታውን አላህንም ይፍራ። ካለበት እዳ ምንም አያጉድል። ያም በእርሱ ላይ እዳው ያለበት የአእምሮም ሆነ የአካል መታወክ ካለበት ወይም በቃሉ ማስፃፍን የማይችል ከሆነ ወኪሉ በትክክል ያስፅፍለት። ከወንዶቻችሁ ሁለትን ምስክሮች አስመስክሩ። ሁለትም ወንዶች በስፍራው ካልተገኙ ለምስክርነት በቂ የሆኑ አንድ ወንድና አንደኛዋ ስትረሳ አንደኛይቱ ሌላዋን ታስታውሳት ዘንድ ሁለት ሴቶች* ይመስክሩ። ምስክሮችም በተጠሩ ጊዜ ከመመስከር እንቢ አይበሉ። (እዳው) ትንሽ ወይም ትልቅ ቢሆንም እስከጊዜው ድረስ ከመፃፍ አትሰልቹ። ይህ ይህን ማድረጋችሁ አላህ ዘንድ በጣም ትክክል ለምስክርነቱም ተዐማኒት የሚያጎናፅፍ ጥርጣሬንም ለማስወገድ በጣም የተመቸ አሰራር ነው። በመካከላችሁ እጅ በእጅ በምትለዋወጡት ንግድ ላይ ግን ባትፅፏት በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም። በተሻሻጣችሁ ጊዜ አስመስክሩ። ፀሐፊም ሆነ ምስክር ባለጉዳዩ ጉዳት ሊያደርስባቸው አይገባም። ይህንን ብትሰሩ በእናንተ በኩል የሚመጣ አመፅ ነው። አላህን ፍሩ። አላህ ያሳውቃችኋል። አላህ ሁሉንም ነገር አዋቂ ነውና።

* ኢስላም የሴትን ምስክርነት ከወንድ ጋር እኩል ያደረገባቸው ጉዳዬች እንዳሉ ሁሉ፤ የሴት ብቻ ምስክርነት የሚሰማባቸው ጉዳዩችም አሉ። ገንዘብ ነክ ነገሮች ላይ ግን አንቀፁ እንደሚመራን አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች መመስከር አለባቸው።

۞ وَإِن كُنتُمْ عَلَىٰ سَفَرٍ وَلَمْ تَجِدُوا۟ كَاتِبًا فَرِهَـٰنٌ مَّقْبُوضَةٌ ۖ فَإِنْ أَمِنَ بَعْضُكُم بَعْضًا فَلْيُؤَدِّ ٱلَّذِى ٱؤْتُمِنَ أَمَـٰنَتَهُۥ وَلْيَتَّقِ ٱللَّهَ رَبَّهُۥ ۗ وَلَا تَكْتُمُوا۟ ٱلشَّهَـٰدَةَ ۚ وَمَن يَكْتُمْهَا فَإِنَّهُۥٓ ءَاثِمٌ قَلْبُهُۥ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ عَلِيمٌ ﴿٢٨٣﴾

**283.** በጉዞ ላይ ብትሆኑና ፀሐፊ ባታገኙ በእጅ የተጨበጡ መተማመኛዎችን ያዙ። ከፊላችሁ ከፊሉን ቢያምን ያ የታመነው ሰው አደራውን በትክክል ያድርስ። አላህንም ጌታውን ይፍራ። ምስክርነትንም አትደብቁ ምስክርነትን የሚደብቃት ሰው ልበ ኃጢአተኛ ነው። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነውና።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (282-283) ኛው ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፦**

1. ብድሮች፤ የዱቤ ግብይቶች፤ ገንዘብ ነክ ስምምነቶችና ውሎች በሙሉ በጹሁፍ ሰፍረው መቀመጥ እንዳለባቸው፤
2. በአንድ ጉዳይ ግንዛቤ ያለው ሰው ለጉዳዩ እንግዳ የሆነን ሰው ማስረዳት የተፈቀደ መሆኑን፤

3. ፍትህ በእያንዳንዱ የሰው ልጅ እንቅስቃሴ ላይ አስፈላጊ ነገር መሆኑን፤
4. በፅሑፍ የሚሰፍሩ ውሎች፤ ግብይቶችና ብድሮች በሙሉ የሚፀድቁት ምስክሮችን ባካተተ መልኩ ሲፃፉ ብቻ መሆኑን፤
5. ለምስክርነትም ሁለት ወንዶች አሊያ አንድ ወንድና ሁለት ሴቶች እንደሚያስፈልጉ፤
6. ብድር መጠኑ ትንሽም ቢሆን በፅሑፍ መቀመጡ ግዴታ እንደሆነ፤
7. እጅ በእጅ የሚደረግ የንግድ ልውውጥና ግብይት በፅሑፍ መስፈሩ ግዴታ እንዳልሆነ እና ቢፃፉ ግን ተመራጭ እንደሆነ፤
8. የንግድ ውሉን ወይም የዱቤዉን ስምምነት ለመፃፍ የተቀመጠውን ፀሐፊም ሆነ ምስክሮች ማዋከብ የተከለከለ መሆኑን፤
9. አላህን መፍራት አዕምሮን አስፍቶ እውቀትን ለመጨመር በር የሚከፍት መሆኑን፤
10. የብድሩ አይነትና መልኩ፤ አሻሻጡ፤ የጊዜ ገደቡ መታወቁ ተገቢ መሆኑን፤
11. የሚሸጠው የታወቀና የተወሰነ መሆን አለበት፤
12. ፀሐፊው ዲን ያለው፤ የሚፅፈውን በአግባቡ . ያለ አድሎ መፃፍ እንዳለበት፤
13. ፅሑፉ የሚለይና ለመረዳት የሚቻል አይነት መሆን አለበት፤
14. በፅሑፍ ማስረጃዎች ከቀረቡ መወሰን እንዳለበት፤
15. ፅሑፍ የሚችለው እንቢ ማለት እንደሌለበት፤
16. ብድር ያለበት የሚነግረንን ብቻ መፃፍ እንዳለበት፤
17. የሚናገረው ተበዳሪው ብቻ መሆኑን፤
18. በእሱ ላይ ያለበትን በሙሉ መናገር እንዳለበት፤
19. አንድ ሰው በራሱ ላይ ብድር አለብኝ ካለ ምንም ሌላ ማስረጃ ሳያስፈልገው ተሰሚ መሆኑን፤
20. ምስክሮች ከተሟሉ መስጠት እንዳለበት፤
21. እንደ ህፃንና የአዕምሮ ዘገምተኛት በመሆኑ ችግር ያለበት ፍትሀዊና አማኝ የሆነ ዘመድ አብሮት መኖር እንዳለበት፤
22. ስለ ገንዘብ ዘመድ መወከል እንደሚቻል፤
23. ሕፃን፤ የአዕምሮ ዘገመተኛና እብድ ብድር አለብን ቢሉ እንደማቻል፤
24. ተወካያቸው በገንዘባቸው መስራት እንደሚችል፤
25. በብድር ሒደት ላይ የሚተማመኑበትን ማቅረብ እንዳለባቸው፤
26. ፁሑፍ መማር እንደሚገባ፤
27. በመዋዋል ጊዜ ሁለት ምስክሮቸን ማቅረብ እንዳለበት፤
28. የሕፃን ምስክርነት እንደማይቻል፤
29. ሴቶች ብቻቸውን መመስከር እንደማይችሉ፤
30. ወንድም ሆነ ሴት አካለ መጠን የልደረሰ ምስክርነት እንደማይችል፤
31. የከሓዲያን ምስክርነት እንደማይቻል፤
32. አንድን ነገር አጢኖ ለማወቅ ወንድ ከሴት እንደሚሻል፤
33. የረሳው ሰው ከአስታወሱት መካድ እንደማይችል፤
34. ምስክርነትን የሚረሳ አስቀድሞ መፃፍ እንዳለበት፤
35. ምስክሩ ከአቅሙ በላይ የሆነ ችግር ከሌለበት ለምስክርነት ወደ ተጠራበት ቦታ መምጣት እንዳለበት፤
36. የምስክርነት መስፈርት ካልተሟላ የመመስከር ግዴታ እንደማይኖርበት፤
37. ያለበትን ብድር ከመፃፍ መሰልቸት እንደሌለበት፤
38. ምስክርነት መፃፍ ህጋዊ የሆነበት ምስጥር፤

39. የተጠራጠረ ሰው ምስክር መሆን እንደማይችል፤
40. የዕለት ሽያጭን አለመፃፍ እንደሚቻልና ማስመስከሩ ግን እንደሚወደድ፤
41. ፀሐፊ ለመፃፍ ዝግጁ ባልሆነበት እሱን ማስቸገር እንደማይቻል፤
42. እንዲሁም ምስክሩ ዝግጁ ባልሆነበት ጊዜ ማስቸገር እንደማይገባው፤
43. ምስክር የሆነ ሰው ብዙ ክፍያም ሆነ ጥቅማ ጥቅም መጠየቅ እንደሌለበት፤
44. እነዚህን ነገሮች መስራት የማመፅ ምልክት ስለመሆኑ፤
45. ማፍቀር፤ መጥላት፤ ንፍቅና፤ እምነት፤ ማመፅ የሚባሉ ባህሪያት በሰዎች ላይ ሊከሰቱና ሊታዩ እንደሚችሉ፤
46. ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ምስክር ሊሆን እንደማይችል እንማራለን።

لِّلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلْأَرْضِۗ وَإِن تُبْدُواْ مَا فِيٓ أَنفُسِكُمْ أَوْ تُخْفُوهُ يُحَاسِبْكُم بِهِ
ٱللَّهُۖ فَيَغْفِرُ لِمَن يَشَآءُ وَيُعَذِّبُ مَن يَشَآءُۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٖ قَدِيرٌ ﴿٢٨٤﴾

**284.** በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለ ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ብትገልፁት ወይም ብትደብቁት አላህ በእርሱ ይቆጣጠራችኋል የሚሻውን ሰው ይምራል። የሚሻውንም ሰው ይቀጣል። አላህ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነውና። (ይተሳሰባችኋል)።

ءَامَنَ ٱلرَّسُولُ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِ مِن رَّبِّهِۦ وَٱلْمُؤْمِنُونَۚ كُلٌّ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ
لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٖ مِّن رُّسُلِهِۦۚ وَقَالُواْ سَمِعْنَا وَأَطَعْنَاۖ غُفْرَانَكَ رَبَّنَا وَإِلَيْكَ ٱلْمَصِيرُ ﴿٢٨٥﴾

**285.** መልዕክተኛው (ሙሐመድ) ከጌታው ወደ እርሱ በተወረደለት ሁሉ አምኗል። ምዕመናንም እንደዚሁ አመኑ። ሁሉም በአላህ፣ በመላዕክቱም፣ በመጽሐፍቱና በመልዕክተኞቹ በሁሉ ከእነርሱ በአንዱም መካከል አንለይም (አንክድም) የሚሉ ሲሆኑ አመኑ። የአላህን ትዕዛዛትንም ሰማን ታዘዝንም አሉ። ጌታችን ሆይ! ምህረትህን እንሻለን። የሁሉም መመለሻ ወደ አንተው ብቻ ነው አሉም።

ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (284-285) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- በዚህ ምዕራፍ አንቀፅ ላይ ያለው ሲወርድ የረሱል (ﷺ) ሕዝቦች ማለትም አቡ በክር፤ ዑመር፤ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን፤ ሙዓዝ ኢብኑ ጀበልና ሌሎችም የመዲና ሰዎች ወደ ነብዩ መጥተው «እስካሁን ካቅማችን ጋር ተመጣጣኝና የምንችለውን የአምልኮ ተግባር ማለትም ሶላት፤ ፆም፤ ጂሃድ፤ ሰደቃ ወዘተ. ከአላህ ታዘን ለመተግበር በቅተናል። ዛሬ ግን የማንችለው ነገር መጣ ይሏቸዋል። ነብዩም «የመፅሐፍ ባለቤቶች ከእናንተ በፊት ሰምተናል ግን አንቀበልም እንዳሉት ልትሉ ፈለጋችሁ እንዴ? ይልቁንም ሰምተናል፤ ታዘናል ምህረትን ስጠን ጌታችን መመለሻችን ወደ አንተ ነው በሉ አሏቸው። ሶሃቦችም ይህን አባባል ተከትለው አስተጋቡ። በዚህም ላይ ተጨንቀው ሳሉ ይህን ተከትሎ የሚቀጥለው አያ ወረደና በዚህ አንቀፅ ላይ ባለው ሕግ ተቃለለ። (ሙስሊም፤ ዋሒዲ፤ ቁርጡቢ እና ኢብኑ ከሲር)

لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا ۚ لَهَا مَا كَسَبَتْ وَعَلَيْهَا مَا ٱكْتَسَبَتْ ۗ رَبَّنَا لَا تُؤَاخِذْنَآ إِن نَّسِينَآ أَوْ أَخْطَأْنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تَحْمِلْ عَلَيْنَآ إِصْرًا كَمَا حَمَلْتَهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِنَا ۚ رَبَّنَا وَلَا تُحَمِّلْنَا مَا لَا طَاقَةَ لَنَا بِهِۦ ۖ وَٱعْفُ عَنَّا وَٱغْفِرْ لَنَا وَٱرْحَمْنَآ ۚ أَنتَ مَوْلَىٰنَا فَٱنصُرْنَا عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٢٨٦﴾

**286.** አላህ የትኛዋንም ነፍስ ከችሎታዋ በላይ አያስገድዳትም። ነፍስ ሁሉ ለሰራችው መልካም ስራ ሁሉ ተገቢው ምንዳ አላት። በእርሷም ላይ ባፈራችው (ኃጢአት) ተገቢው ቅጣት አለባት። (ሙስሊሞች) ጌታችን ሆይ! ብንረሳ ወይም ብንሳሳት (አትቅጣን)። ጌታችን ሆይ! ከባድ ሸክምን ከእኛ በፊት በነበሩት ህዝቦች ላይ እንደጫንከው ሁሉ በእኛ ላይ አትጫንብን። ጌታችን ሆይ! ለእኛ ችሎታ የሌለንን ነገር አታሸክመን። ለእኛም ይቅርታ አድርግልን። ለእኛም ምህረትን አድርግልን። እዘንልንም። ረዳታችን አንተ ብቻ ነህና። በከሓዲ ሕዝቦች ላይም እርዳን (ድልን አጎናፅፈን) (አሉ)።*

✳ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ መስዑድ እንዳስተላለፉት፡- የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሌሊት ላይ የመጨረሻዎቹን ሁለት የላሟ ምዕራፍ አናቅፅ ያነበበ ለእሱ በቂው ነው»

ከላሟ ምዕራፍ (286) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- (284) ኛው አንቀፅ በወረደበት ጊዜ ሶሃቦች ትዕዛዙን መፈፀም ከበዳቸው እና በውስጣችን ባሰብነው ሁሉ ከተመረመርንማ አለቅና ሲሉ ነብዩ ከእናንተ በፊት የነበሩ የመፅሐፍ ሰዎች እንዳሉት ልትሉ ነው እንጄ ሰማን ታዘዝን በሉ አሏቸው። እነርሱም ያለ ምንም ማመንታት ሰማን ታዘዝን ሲሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደና የሻረው።

**ከላሟ ምዕራፍ ከአንቀፅ (283-286) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካካል ዋና ዋናዎች፡-**

1. ብድር የሚወስድ ሰው ዋስትና የሚሆን ንብረት ማስያዙ የተፈቀደ መሆኑን፤
2. በአበዳሪውና በተበዳሪው መካከል መተማመን ካለ መያዣ ባይኖርም ችግር እንደሌለበት፤
3. ለምስክርነት የተጠራ ሰው ያየውን ነገር መደበቁ የተከለከለ መሆኑን፤
4. ሰው በልቡ ውስጥ በደበቀው ተንኮልና መጥፎ ነገር ተቀጪ መሆኑን፤
5. የእምነት መሰረቶች በአላህ፤ በመልአክት፤ በመፅሐፍትና በነብያት ሁሉ ማመን መሆኑን፤
6. አላህን እና የእርሱን መልዕክተኛን (ﷺ) መታዘዝ በሙስሊሞች ላይ የተደነገገ ግዴታ መሆኑን፤
7. የመልዕክተኛው ተከታይ ህዝብ ከህዝቦች ሁሉ ይበልጥ የተመረጡ ህዝቦች መሆናቸውን፤
8. የአላህ ዲን ገርና ለመተግበር ፈፅሞ የማያስቸግር መሆኑን፤
9. ኸይር የሰራ ሰው ዋጋው ኸይር፤ መጥፎ የሰራም እንዲሁ ምንዳው መጥፎ መሆኑን።
10. በስህተት ወይም በመርሳት የሚፈፀም ወንጀል ነክ ድርጊቶች ሁሉ በአላህ ዘንድ እንደማያስጠይቁ፤
11. በልብ ውስጥ ትዝ በሚሉ መጥፎ ሀሳቦች ምክንያት የሰው ልጅ እንደማይጠየቅ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የላሟ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (3)
# የዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ
## (ሱረቱ ኣሊ ዒምራን)

سورة آل عمران

### የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ (200) ናቸው።
### የሱረቱ ኣሊ ዒምራን መግቢያ

ምዕራፉ ከሚያተኩርባቸው ዋና ዋና ትምህርቶች የሚከተሉት ናቸው:- እምነትን የሚያስተምሩ አያሌ ማስረጃዎችን በየቦታው መደርደርና ከሰዎች መካከል እውነትን የሚከተሉት ክፍሎች አናሳ መሆናቸውን በግልፅ ማስመር፤ ስለ ቁርኣን ትልቅነት፤ የመፅሐፍ ባለቤቶች በቁርኣን ላይም ሆነ በነብዩ ላይ እያወሩ ያሉትን አሉቧልታዎችን ማስተባበል፤ ስለ ነብዩ (ﷺ) ትልቅነትና በእሳቸውም ዙሪያ የመፅሐፍ ባለቤቶች እያስወሩ ያሉትን አሉቧልታዎችን ማስተባበል፤ የቁርኣን አናቅፅ ለስንት እንደሚከፈሉና ሰዎችም ከመቀበል አኳያ እንደዚሁ እንደሚለያዩ፤ ስለ ኢስላም ትልቅነት፤ የተውራትንና የኢንጂልን ምንነት፤ ስለ ኢስላም የተናገሩትን የምስክርነት ቃል ይሰጣል፤ ስለ ነብዩ ዒሳና ስለ ቤተሰቦቻቸው፤ ስለ ነጅራን መልዕክተኞችና ከነብዩ (ﷺ) ጋር ስላደረጉት ውይይት፤ ብዛት ያላቸውን የነብዩን (ﷺ) የዘመቻ ውሏቸውን መጠቆምና ሌሎችንም ዋና ዋና ጉዳዮችን ይዳስሳል። ሁለቱ ተከታታይ ምእራፎች ማለትም: (1) የላሟ ምዕራፍ እና (2) የዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ የሚመሳሰሉበት ብዙ ጉዳዮች አላቸው። ከእነዚህም መካከል

1. ሁለቱም ስለ መፅሐፍና ህዝቦች አተገባበር በማውሳት መጀመራቸው መሆኑ ነው።
   ምክኒያቱም በላሟ ምዕራፍ ላይ በትክክል የተገበሩትን፤ በግልፅ እንቢ ያሉትን እና ወላዋዬችን እንዳ ወሳ ሁሉ በዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍም ላይ በትክክል የሚቀበሉትን እና ግልፅ ያልሆኑትን ብቻ እየፈለጉ የሚከታተሉትን አዉስቷል።
2. በላሟ ምዕራፍ ላይ የአባታችንን የአደምን አፈጣጠር እንዳወሳ ሁሉ በዒምራን ምዕራፍ ላይ የነብዩ ዒሳን አፈጣጠር በማውሳት የሁለቱን ተመሳሳይነት ማስታወስ፤
3. በሁለቱም ዉስጥ የመፅሐፍ ባለቤቶችን የተከራከረ ሲሆን በላሟ ዉስጥ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የአይሁዳው ቡድን ሲሆን፤ በዒምራን ምዕራፍ ዉስጥ ግን በክርስቲያኖች ላይ መሆኑ ቅደም ተከተላቸዉን የጠበቀ በመሆኑ፤
4. በሁለቱም ምእራፎች መደምደሚያ ላይ ዱዓ በመኖሩ፤
5. የሁለተኛው ምዕራፍ ማብቂያ ከመጀመሪያው መነሻ ጋር መጣጣሙ የሚሉት ይገኙበታል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓ ﴿١﴾

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም፤* (በነዚህ ፊደላት ምን እንደፈለገ አላህ ራሱ ብቻ ያውቃል።)

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡحَيُّ ٱلۡقَيُّومُ ﴿٢﴾ نَزَّلَ عَلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ مُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيۡهِ وَأَنزَلَ ٱلتَّوۡرَىٰةَ وَٱلۡإِنجِيلَ ﴿٣﴾ مِن قَبۡلُ هُدٗى لِّلنَّاسِ وَأَنزَلَ ٱلۡفُرۡقَانَۗ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ لَهُمۡ عَذَابٞ شَدِيدٞۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٞ ذُو ٱنتِقَامٍ ﴿٤﴾

**2-4.** አላህ ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ አምላክ የለም። አላህ ህያው፤ በራሱ የተብቃቃና የሁሉ ነገር አስተናባሪ (የፍጡራን ተንከባካቢ) ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከእርሱ በፊት ያሉትን መጽሐፍት የሚያረጋግጥ ሲሆን ቁርኣንን በአንተ ላይ ከፋፍሎ በእውነት አወረደው። ከቁርኣን በፊት ለሰዎች መሪ አድርጎ ተውራትንና ኢንጅልን አውርዷል። (በእውነትና በውሸት መካከል መለያ የሆነውን) ፉርቃንንም አወረደ። እነዚያ በአላህ አናቅፅ የካዱ ሰዎች ሁሉ ብርቱ ቅጣት አለባቸው። አላህ አሸናፊ፤ አስተባባዩችን ተበቃይም ነውና።

የዚህ ምዕራፍከ (1-3) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክኒያት፡- ከነቢዩ ጋር በእምነት ጉዳይ ሊነጋገሩ ወደ መዲና ተጉዘው በነበሩ (60) የሚሆኑ የነጅራን ክርስቲያኖች ምክኒያት ነው ተብሏል። (ኢብኑ ጀሪር፤ ኢብኑ ኢስሓቅ፤ ኢብኑል -ሙንዚር እና ኢብኑ ከሲር)

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَخۡفَىٰ عَلَيۡهِ شَيۡءٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا فِي ٱلسَّمَآءِ ﴿٥﴾ هُوَ ٱلَّذِي يُصَوِّرُكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡحَامِ كَيۡفَ يَشَآءُۚ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ﴿٦﴾

**5-6.** አላህ በምድርም ሆነ በሰማይ ምንም ነገር አይሸሸገውም። (ሙስሊሞች ሆይ!) እርሱ ያ! (አላህ) በማህፀኖች ውስጥ እንደፈለገው አድርጎ የሚቀርፃችሁ ነው። ከእርሱ ከአሸናፊዉና፤ ከጥበበኛው ጌታ በስተቀር ሌላ ትክክለኛ አምላክ በፍፁም የለም።

هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ عَلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ مِنۡهُ ءَايَٰتٞ مُّحۡكَمَٰتٌ هُنَّ أُمُّ ٱلۡكِتَٰبِ وَأُخَرُ مُتَشَٰبِهَٰتٞۖ فَأَمَّا
ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِمۡ زَيۡغٞ فَيَتَّبِعُونَ مَا تَشَٰبَهَ مِنۡهُ ٱبۡتِغَآءَ ٱلۡفِتۡنَةِ وَٱبۡتِغَآءَ تَأۡوِيلِهِۦۖ وَمَا يَعۡلَمُ
تَأۡوِيلَهُۥٓ إِلَّا ٱللَّهُۗ وَٱلرَّٰسِخُونَ فِي ٱلۡعِلۡمِ يَقُولُونَ ءَامَنَّا بِهِۦ كُلّٞ مِّنۡ عِندِ رَبِّنَاۗ وَمَا يَذَّكَّرُ إِلَّآ
أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٧ رَبَّنَا لَا تُزِغۡ قُلُوبَنَا بَعۡدَ إِذۡ هَدَيۡتَنَا وَهَبۡ لَنَا مِن لَّدُنكَ رَحۡمَةًۚ إِنَّكَ أَنتَ
ٱلۡوَهَّابُ ٨ رَبَّنَآ إِنَّكَ جَامِعُ ٱلنَّاسِ لِيَوۡمٖ لَّا رَيۡبَ فِيهِۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُخۡلِفُ ٱلۡمِيعَادَ ٩

**7-9.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (እርሱ) (አላህ) ያ! በአንተ ላይ መጽሐፍን- (ቁርኣንን) ያወረደ ነው። ከርሱ (ከመፅሐፉም) ውስጥ ግልፅ የሆኑ አንቀፆች አሉ። እነርሱም የመጽሐፉ መሰረቶች (ዋና ዋልታዎች) ናቸው። ሌሎች ደግሞ አሻሚ ትርጉም ያላቸው አሉ። እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው ሰዎች ሁሉ ሌሎችን ማሳሳት በማሰብና ትርጉምን በሻቸው ለመለወጥ ሲሉ ከቁርኣን አንቀፆች መካከል አሻሚ ትርጉሞች (ተመሳሳይነት) ያሏቸውን አንቀፆች ብቻ ይከታተላሉ*1። የዚህን ክፍል ትክክለኛ ትርጉሙን አላህ ብቻ እንጂ ሌላ ማንም አያውቀውም። እነዚያ በእውቀት የጠለቁ ክፍሎች ግን በእርሱ አምነናል። ሁሉም ከጌታችን ዘንድ ነው የመጣው ይላሉ። (በእንዲህ ዓይነቱ ነገር) የአእምሮ ባለቤቶች እንጂ ሌላው አይገሰፅም። እነርሱ ጌታችን ሆይ! ቅኑን መንገድ ከመራኸን በኋላ ልቦቻችንን*2 ወደ መጥፎ አታዘንብልብን። ከአንተ ዘንድ የሆነን ችሮታ ስጠን። አንተ በጣም ለጋስ ነህና ይላሉ። ጌታችን ሆይ! አንተ በዚያ ለመምጣቱ ጥርጥር በሌለበት ቀን ሰውን ሁሉ ሰብሳቢ ነህ። ምን ጊዜም አላህ ቀጠሮን አያፈርስምና።

*1 ይህን አስመልክተው ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ለእናታችን አይሻ ሲነግሯቸው «እነዚያ አሻሚዎችን የሚከተሉ ሰዎችን ካየሽ አላህ ያወሳቸው ሰዎች መሆናቸዉን እወቂ። እናም ተጠንቀቋቸው» ብለዋል።

*2 ልብ የሰው ልጆች አካሎች ሁሉ ወሳኙ ክፍል ነው። እሱ ከተስተካከለ ሁሉም አካል ይስተካከላል። ይህን አስመልክቶ ነብዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «አዋጅ! በየአካላችን ውስጥ አንዲት ብጣሽ ስጋ አለች እሷ ከተስተካከለች ሙሉ አካል ይስተካከላል። እሷ ከተበላሸች ደግሞ ሙሉ አካል ይበላሻል። እሷም ልብ ናት» ብለዋል።

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-9) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ብቸኛ ፈጣሪነትና አምላክነት በአዕምሮና በተፈጥሮ ማስረጃዎች የተረጋገጠ መሆኑን፤
2. ከአላህ ስሞች አራቱን፤ አል-ሐዩ፤ አል-ቀዩም፤ አል-ዐዚዝ፤ አል ሐኪም፤ አል ወሃብ የሚሉትን ማውሳቱን፤
3. ሁሉም ፍጡር እሱን እንደሚከጅል፤
4. አወረደ በሚለው ቃሉ የአላህን የበላይነት ማስረዳቱን፤

5. ቁርኣን ከእርሱ የወረደ መልዕክት መሆኑን፤
6. በአንተ ላይ አወረድኩት በማለት ነብዩ የእርሱ ትክክለኛ መልዕክተኛ መሆናቸውን፤
7. አዛኙ አላህ በየጊዜው ለሰዎች መመሪያ ማውረዱንና ለሕዝቦች በሙሉ ትክክለኛ መረጃ ማቅረቡን፤
8. ቁርኣንም ሆነ የቁርኣን አስተምህሮት ሐቅ መሆኑን፤
9. ትክክለኛው የተውራትም ሆነ ትክክለኛው የኢንጂል አስተምህሮት ሐቅ መሆኑን፤
10. የተውራትም ሆነ የኢንጂል አስተምህሮት በቁርኣን አስተምህሮት የተሻረ መሆኑን፤
11. ቀደምት መፅሐፍት ስለ ቁርኣን የተናገሩ መሆናቸዉን፤
12. ነብዩ ዒሳ የተከበሩ ትክክለኛ የአላህ መልዕክተኛ እንጂ ራሳቸው አምላክ አለመሆናቸውን፤
13. የከሓዲያን ቅጣት ምን ያህል ከብደት እንዳለው፤
14. ሰዎች ከሓዲያንና አማኞች ተብለው ለሁለት እንሚከፈሉ፤
15. አላህ የማያውቀው ነገር አንድም እንደሌለ፤
16. ከአላህ ሌላ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ማንም እንደሌለ፤
17. ያ! ፍጡራንን በማህፀን ውስጥ እያሉ የየራሳቸውን ቅርፅ የሰጠ አላህ ወደር የለሽ ችሎታ እንዳለው፤
18. ያ! ፍጡራንን በማህፀን ዉስጥ እያሉ ተገቢ ስንቃቸውን በማዘጋጀት የሚንከባከብ ጌታ አላህ ወደር የለሽ ሩህሩህ መሆኑን፤
19. ውፍረት፤ ቅጥነት፤ ቅላት፤ ጥቁረት፤ ድህነት፤ ፀጋ...በሙሉ የሚሆነው በአንድ አላህ ፍቃድ ብቻ መሆኑን፤
20. አላህ መሻት እንዳለው፤
21. ይህ ቁርኣን የአላህ ቃል መሆኑን፤
22. የአላህን የበላይነት በግልፅ ማስረዳት፤
23. በቁርኣን ውስጥ በግልፅ የተብራሩ ድንጋጌዎች እና ማብራሪያ የሚያስፈልጋቸው ተመሳሳይነት ያላቸው አናቅፅ እንዳሉ፤
24. ማብራሪያ የሚሹ አናቅፅን በስሜታቸው ትርጓሜ የሚከተሉ ሰዎች በልባቸው ውስጥ ጥመት ያለባቸው እንደሆኑ፤
25. አሻሚዎችን ለመረዳት ግልፆችን በዋነኝነት መያዝ እንደሚያስፈልግ፤
26. በቁርኣን ዉስጥ ይህ አይነቱ ክፍል መኖሩ ለፈተና እንደሆነ፤
27. አሻሚዎችን እየመረጡ ህዝብን ማሳሳት የጠማሞች ዋና መለያ መሆኑን፤
28. እነዚህ አይነት ሰዎች በዚህ የሚፈልጉት አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን መፈተን በሌላ ጊዜ ደግሞ ወደ ሚፈልጉት መሳብ እንደሆነ፤
29. ጥልቅ እውቀት ሁል ጊዜም ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነና ጥልቅ እውቀት ያላቸው ሰዎች በአላህ ዘንድ ያላቸው ማዕረግ፤
30. በዚህ ቁርኣን የሚጠቀሙበት ባለ አዕምሮዎች እንደሆኑ፤
31. የሰዎች ማሰቢያ የሆነው አዕምሮ በዳበረ ቁጥር በቁርኣን የመጠቀሙ አቅም እያደገ እንደሚሄድ፤
32. ከቁርኣን ዉስጥ አላህ ብቻ የሚያውቃቸው ነገሮች እንዳሉ፤
33. የአላህ እውቀት ስፋትን እንድናስተነትን ማድረግ፤

34. ከእነዚህ በተጨማሪ ከመሞት በኋላ ለሚጠብቀን አኼራዊ ሕይወት ዳግም ወደ ህይወት የምንመለስ መሆኑን፤
35. በዚህ አይነት ዱዓ ማድረግ ተገቢ መሆኑን፤
36. ዱዓን ሲያደርጉ ጌታዬ በሚል ቃል መጀመሩ፤
37. የሰው ልጅ ልቡን መቆጣጠር እንደማይችልና በዚህ ጉዳይ ሁልጊዜም አላህን መለመን እንደሚገባን፤
38. ልብ ሁለት ባህሪ እንዳለውና በቀጥተኛው መንገድ ለመሄድ አላህን መለመን እንደሚያስፈልገው፤
39. በአላህ ስሞች መወሰል ተገቢ መሆኑን፤
40. የትንሳኤ ቀን መምጣቱ አይቀሬ መሆኑን፤
41. ሁሉን ነገር የሚያደርገው አላህ በትንሳኤ ዕለትም በአንዲት ቃል ሁሉን መሰብሰብ እንደሚችል እንማራለን።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَن تُغۡنِيَ عَنۡهُمۡ أَمۡوَٰلُهُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُهُم مِّنَ ٱللَّهِ شَيۡـٔٗاۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ وَقُودُ ٱلنَّارِ ١٠ كَدَأۡبِ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا فَأَخَذَهُمُ ٱللَّهُ بِذُنُوبِهِمۡۗ وَٱللَّهُ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ١١

**10-11.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ ገንዘቦቻቸውና ልጆቻቸው ከአላህ (ቅጣት) ምንም ያክል አያስጥሏቸውም። እነዚያ እነርሱ የእሳት ማገዶዎች ናቸው። ምሳሌያቸው ልክ እንደ ፈርዖን ቤተሰቦችና እንደነዚያ ከበፊታቸዉም እንደነበሩት ሕዝቦች ልማድ ነው። በአንቀፆቻችን አስተባበሉ። እናም አላህ በኃጢአቶቻቸው ቀጣቸው። አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና።

قُل لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ سَتُغۡلَبُونَ وَتُحۡشَرُونَ إِلَىٰ جَهَنَّمَۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمِهَادُ ١٢ قَدۡ كَانَ لَكُمۡ ءَايَةٞ فِي فِئَتَيۡنِ ٱلۡتَقَتَاۖ فِئَةٞ تُقَٰتِلُ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَأُخۡرَىٰ كَافِرَةٞ يَرَوۡنَهُم مِّثۡلَيۡهِمۡ رَأۡيَ ٱلۡعَيۡنِۚ وَٱللَّهُ يُؤَيِّدُ بِنَصۡرِهِۦ مَن يَشَآءُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَعِبۡرَةٗ لِّأُوْلِي ٱلۡأَبۡصَٰرِ ١٣

**12-13.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነዚያ በአላህ ለካዱ ሰዎች «በቅርብ ጊዜ ትሸነፋላችሁ። ከዚያ ገሀነም ትሰበሰባላችሁ። ምንጣፊቱም ገሀነም ምን ትከፋ!» በላቸው። (ከሓዲያን ሆይ!) በእነዚያ (የበድር ቀን) በተጋጠሙት ሁለት ቡድኖች ለእናንተ በእርግጥ ተዓምር አለ። አንደኛዋ ቡድን በአላህ መንገድ ትጋደላለች። ሌላይቱ ቡድን ደግሞ ከሓዲ ናት። ከሐዲያን አማኞቹን በዓይን አስተያየት እጥፋቸው ሆኖ ያዩዋቸዋል (በቁጥር የነርሱ እጥፍ ሁነው በአይናቸው ተመለከቷቸው)። አላህ በእርዳታው የሚሻውን ሰው ሁሉ ያበረታልና። በዚህ ውስጥ የማስተዋል ባለቤቶች ሁሉ በእርግጥ መገሰጫ አለበት።

زُيِّنَ لِلنَّاسِ حُبُّ ٱلشَّهَوَٰتِ مِنَ ٱلنِّسَآءِ وَٱلْبَنِينَ وَٱلْقَنَٰطِيرِ ٱلْمُقَنطَرَةِ مِنَ ٱلذَّهَبِ وَٱلْفِضَّةِ
وَٱلْخَيْلِ ٱلْمُسَوَّمَةِ وَٱلْأَنْعَٰمِ وَٱلْحَرْثِۗ ذَٰلِكَ مَتَٰعُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَاۖ وَٱللَّهُ عِندَهُۥ حُسْنُ ٱلْمَـَٔابِ ١٤

**14.** ከሴቶችና ከወንዶች ልጆች፤ ከወርቅና ከብር፤ ከተከማቹ ገንዘቦች፤ ከተሰማሩ ፈረሶች፤ ከግመል ከከብትና ከፍየል፤ ከአዝመራም የሆኑ ፍላጎቶችን መውደድ ለሰዎች ተሸለመላቸው (ከሰዎች ዘንድ የተወደዱ ናቸው)። ይህ ሁሉ የቅርቢቱ ሕይወት መጠቃቀሚያ ብቻ ነው። አላህም እርሱ ዘንድ መልካም የሆነ መመለሻ (ገነት) አለው።

* قُلْ أَؤُنَبِّئُكُم بِخَيْرٍ مِّن ذَٰلِكُمْۖ لِلَّذِينَ ٱتَّقَوْاْ عِندَ رَبِّهِمْ جَنَّٰتٌ تَجْرِي مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ
خَٰلِدِينَ فِيهَا وَأَزْوَٰجٌ مُّطَهَّرَةٌ وَرِضْوَٰنٌ مِّنَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ بَصِيرُۢ بِٱلْعِبَادِ ١٥ ٱلَّذِينَ يَقُولُونَ
رَبَّنَآ إِنَّنَآ ءَامَنَّا فَٱغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا وَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٦ ٱلصَّٰبِرِينَ وَٱلصَّٰدِقِينَ وَٱلْقَٰنِتِينَ
وَٱلْمُنفِقِينَ وَٱلْمُسْتَغْفِرِينَ بِٱلْأَسْحَارِ ١٧

**15-17.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዚህ ከተዋበላችሁ ጉዳይ የሚበልጥን ልንገራችሁን? እርሱም ለእነዚያ አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ሁሉ በጌታቸው ዘንድ በስራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው✴ ገነቶች በውስጧ ሁልጊዜ ነዋሪዎች ሲሆኑ ንፁህ ሚስቶችና ከአላህ የሆነ ውዴታም አለላቸው። አላህ አገልጋዮቹን ተመልካች ነውና በላቸው። እነዚያ ጌታችን ሆይ!እኛ በአንተ አመንን ኃጢአቶቻችንን ማርልን። የእሳትን ቅጣት ጠብቀን የሚሉ ናቸው። እነርሱም ታጋሾች፣ እውነተኞች፣ ታዛዦች፣ ለጋሾችና በሌሊት መጨረሻዎች ሰዓታት ላይ አላህን ምህረትን የሚለምኑ (የሚማጸኑ) ናቸው።

✴ ይህን እውነታ ከሚያብራሩ ሐዲሶች መካከል ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) «በአኼራ ሞት የለም። የጀነት ሰዎች ጀነት ወዲያው እንደገቡም ያለሞት ሁል ጊዜ ኗሪ ናችሁ» ይባላሉ፤ ከዚያም ይደሰታሉ። ነብዩ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «የጀነት ሰዎች ምንጊዜም ሳይከፉችሁ በደስታ ትኖራላችሁ ምንጊዜም ሳያማችሁ በጤና ትኖራላችሁ። ሁልጊዜም ሳታረጁ ወጣት ሆናችሁ ትኖራለችሁ። ምን ጊዜም ሳትሞቱ ህያው ትሆናላችሁ» እንዳሉት ሁሉ ዘላለም ኗሪዎች ናቸው።

شَهِدَ ٱللَّهُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ وَأُوْلُواْ ٱلْعِلْمِ قَآئِمَۢا بِٱلْقِسْطِۚ
لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ١٨

**18.** አላህ በማስተካከል ቀጥ ያለ አስተናባሪ ሲሆን ከእርሱ በስተቀር ሌላ ትክክለኛ አምላክ የሌለ መሆኑን ለፍጡሩ ሁሉ መሰከረ። መላዕክና የእውቀት ባለቤቶች ከእርሱ በስተቀር ሌላ ትክክለኛ አምላክ የሌለ መሆኑን እንደዚሁም መሰከሩ። ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

إِنَّ ٱلدِّينَ عِندَ ٱللَّهِ ٱلۡإِسۡلَٰمُۗ وَمَا ٱخۡتَلَفَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّا مِنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَهُمُ
ٱلۡعِلۡمُ بَغۡيَۢا بَيۡنَهُمۡۗ وَمَن يَكۡفُرۡ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ فَإِنَّ ٱللَّهَ سَرِيعُ ٱلۡحِسَابِ ١٩

**19.** አላህ ዘንድ የተወደደው ሀይማኖት ኢስላም ብቻ ነው። እነዚያ መጽሐፉን የተሰጡ ሰዎች በመካከላቸው ባለው የምቀኝነት ችግር እውቀቱ ከመጣላቸው በኋላ እንጂ (ስለ ኢስላም) አልተለያዩም። በአላህ አንቀፆች ለሚክድ ሰው ሁሉ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው።

فَإِنۡ حَآجُّوكَ فَقُلۡ أَسۡلَمۡتُ وَجۡهِيَ لِلَّهِ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِۗ وَقُل لِّلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡأُمِّيِّـۧنَ
ءَأَسۡلَمۡتُمۡۚ فَإِنۡ أَسۡلَمُواْ فَقَدِ ٱهۡتَدَواْۖ وَّإِن تَوَلَّوۡاْ فَإِنَّمَا عَلَيۡكَ ٱلۡبَلَٰغُۗ وَٱللَّهُ بَصِيرُۢ بِٱلۡعِبَادِ ٢٠

**20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመፅሐፍ ባለቤቶች ቢከራከሩህ ፊቴን ለአላህ ብቻ ሰጠሁ። የተከተሉኝም ሰዎች (እንደዚሁ ለአላህ ብቻ ሰጡ) በላቸው። ለእነዚያም መጽሐፉን ለተሰጡ ሰዎችና ለመሃይማኑ (ዐረቦች)፡- ሰለማችሁን? በላቸው። ቢሰልሙም በእርግጥ ወደቀናው መንገድ ተመሩ። እምቢ ቢሉ ግን አንተ ላይ ያለብህ መልዕክትን ማድረስ ብቻ ነው። አላህ ባሮቹን ተመልካች ነውና።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكۡفُرُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَيَقۡتُلُونَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ بِغَيۡرِ حَقّٖ وَيَقۡتُلُونَ ٱلَّذِينَ يَأۡمُرُونَ
بِٱلۡقِسۡطِ مِنَ ٱلنَّاسِ فَبَشِّرۡهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ٢١ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ حَبِطَتۡ أَعۡمَٰلُهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَا
وَٱلۡأٓخِرَةِ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ٢٢

**21-22.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ አንቀፆች የሚክዱ፣ ነብያትንም ያለ አግባብ የሚገድሉ፣ ከሰዎችም ውስጥ እነዚያን በትክክለኛነት የሚያዙትን የሚገድሉ በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው። እነዚያ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ስራዎቻቸው የተበላሹ ናቸው። ለእነርሱም ምንም ረዳቶች የሏቸውም።

أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ أُوتُواْ نَصِيبٗا مِّنَ ٱلۡكِتَٰبِ يُدۡعَوۡنَ إِلَىٰ كِتَٰبِ ٱللَّهِ لِيَحۡكُمَ بَيۡنَهُمۡ
ثُمَّ يَتَوَلَّىٰ فَرِيقٞ مِّنۡهُمۡ وَهُم مُّعۡرِضُونَ ٢٣ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ قَالُواْ لَن تَمَسَّنَا ٱلنَّارُ إِلَّآ أَيَّامٗا
مَّعۡدُودَٰتٖۖ وَغَرَّهُمۡ فِي دِينِهِم مَّا كَانُواْ يَفۡتَرُونَ ٢٤ فَكَيۡفَ إِذَا جَمَعۡنَٰهُمۡ لِيَوۡمٖ لَّا رَيۡبَ فِيهِ
وَوُفِّيَتۡ كُلُّ نَفۡسٖ مَّا كَسَبَتۡ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ ٢٥

**23-25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ ከመጽሐፍ (ትምህርት) እድልን ወደ ተሰጡት ሰዎች አላየህምን? ወደ አላህ መጽሐፍ በመካከላቸው ይፈረድ ዘንድ ይጠራሉ። ከዚያ ከእነርሱ ገሚሶቹ (ከፊሎቹ) እውነቱን ወደ ጎን የተው ሆነው ይሸሻሉ። ይህም እነርሱ የገሀነም እሳት የተቆጠሩ ቀናትን እንጂ አትነካንም በማለታቸው ነው። በሀይማኖታቸውም ይቀጣጥፉት የነበሩት ነገር አታለላቸው። በእርሱ መምጣት ጥርጥር የሌለበት በሆነው ቀን በሰበሰብናቸውና ነፍስ ሁሉ የሰራችውን ስራ በተሞላች ጊዜ እንዴት ይሆናሉ? እነርሱም አይበደሉም።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (23) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) አይሁዶችን ወደዚህ ሰላም በጠሯቸው ጊዜ ኑዐይም ቢን አምርና ሃሪስ ቢን ዘይድ የተባሉ ከምሁራኖች ጋር እንከራከር በማለት በጋበዟቸው ወቅት ነብዩ (ﷺ) ወደ አላህ መፅሐፍ ነው እንጂ ሲሉ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

قُلِ ٱللَّهُمَّ مَٰلِكَ ٱلْمُلْكِ تُؤْتِى ٱلْمُلْكَ مَن تَشَآءُ وَتَنزِعُ ٱلْمُلْكَ مِمَّن تَشَآءُ وَتُعِزُّ مَن تَشَآءُ
وَتُذِلُّ مَن تَشَآءُ ۖ بِيَدِكَ ٱلْخَيْرُ ۖ إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٢٦﴾ تُولِجُ ٱلَّيْلَ فِى ٱلنَّهَارِ وَتُولِجُ
ٱلنَّهَارَ فِى ٱلَّيْلِ ۖ وَتُخْرِجُ ٱلْحَىَّ مِنَ ٱلْمَيِّتِ وَتُخْرِجُ ٱلْمَيِّتَ مِنَ ٱلْحَىِّ ۖ
وَتَرْزُقُ مَن تَشَآءُ بِغَيْرِ حِسَابٍ ﴿٢٧﴾

**26-27.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የንግስና ባለቤት የሆንከው አላህ ሆይ! ለምትሻው ሰው ንግስና ትሰጣለህ። ከምትሻውም ሰው ንግስናን ትገፋለህ። የምትሻውንም ሰው ታልቃለህ። (ታበልጣለህ)። የምትሻውንም ሰው ደግሞ ታዋርዳለህ። መልካም ነገር ሁሉ በእጅህ ብቻ ነው። አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና በል። ሌሊቱን በቀን ውስጥ ታስገባለህ። ቀኑንም በሌሊት ውስጥ ታስገባለህ። ሕያውንም ከሙት ውስጥ ታወጣለህ። ሙታንንም ከሕያው ውስጥ ታወጣለህ ለምትሻው ሰው ሁሉ መጠን የለሽ ሲሳይ ትሰጣለህ በል።

لَّا يَتَّخِذِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلْكَٰفِرِينَ أَوْلِيَآءَ مِن دُونِ ٱلْمُؤْمِنِينَ ۖ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ فَلَيْسَ مِنَ
ٱللَّهِ فِى شَىْءٍ إِلَّآ أَن تَتَّقُوا۟ مِنْهُمْ تُقَىٰةً ۗ وَيُحَذِّرُكُمُ ٱللَّهُ نَفْسَهُۥ ۗ وَإِلَى ٱللَّهِ ٱلْمَصِيرُ ﴿٢٨﴾

**28.** አማኞች ከሐዲያንን ከአማኞች ሌላ ረዳቶች አድርገው አይያዙ። ይህንን የሚሰራ ሰው ሁሉ ከአላህ ሀይማኖት በምንም ውስጥ አይደለም። ከእነርሱ መጠበቅን ብትጠበቁ እንጂ። አላህ በእራሱ ከእሱው ቅጣት ያስጠነቅቃችኋል። የሁሉ መመለሻ ወደ አላህ ብቻ ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (28) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ አይሁዶች የቀድሞ ጓደኛ ወዳጅ የነበሩ አንሷሮች በእምነታቸው ሊፈትኗቸው ሲከታተሏቸው እነዚህን አይሁዶች ተጠንቀቋቸው እያሉ ሲመክሯቸው ችላ ስላሉ ነው። (ቡኻሪ)

قُلْ إِن تُخْفُوا۟ مَا فِى صُدُورِكُمْ أَوْ تُبْدُوهُ يَعْلَمْهُ ٱللَّهُ ۗ
وَيَعْلَمُ مَا فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٢٩﴾

**29.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በደረቶቻችሁ (በልቦቻችሁ) ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ብትደብቁት ወይም ብትገልፁት አላህ ያውቀዋል። በሰማያት ውስጥ ያለውንና በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው በል።

يَوْمَ تَجِدُ كُلُّ نَفْسٍ مَّا عَمِلَتْ مِنْ خَيْرٍ مُّحْضَرًا وَمَا عَمِلَتْ مِن سُوٓءٍ تَوَدُّ لَوْ أَنَّ بَيْنَهَا
وَبَيْنَهُۥٓ أَمَدًۢا بَعِيدًا ۗ وَيُحَذِّرُكُمُ ٱللَّهُ نَفْسَهُۥ ۗ وَٱللَّهُ رَءُوفٌۢ بِٱلْعِبَادِ ﴿٣٠﴾

**30.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያን ነፍስ ሁሉ ከመልካም ነገር የሰራችውን የቀረበ ሆኖ የምታገኝበትን ቀን (አስታውስ)። ከመጥፎም የሰራችው በእርሷና በእርሱ (በኃጢአቱ) መካከል በጣም የሰፋ ርቀት ቢኖር ትመኛለች። አላህ እራሱን በራሱ ያስጠነቅቃችኋልና። አላህ ለባሮቹ ሩህሩህ ነውና።

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (10-30) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኩራትና ትዕቢት መጨረሻው ለአስከፊ ውድቀት እንደሚዳርግ፤
2. ኩፍር ለቂያማ ቀን አስከፊ ቅጣት የሚያበቃ ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
3. ገንዘብ፤ ልጆች፤ መሳሪያዎችና ቁሳዊ ሀብቶች የቱንም ያህል ቢበዙ ከአላህ ቅጣት የሚያድኑ እንዳልሆኑ፤
4. አማኞች ግን በገንዘብ፤ በልጆች እንደሚጠቀሙ፤
5. እሳት ለከሓዲያን የተዘጋጀ መሆኑን፤
6. ከሓዲያን በምድር ላይ ሀብትን ልጆችን እንደሚያፈሩ፤
7. በየጊዜው ያሉ ከሓዲያን ባህሪያቸው አንድ መሆኑን፤
8. ፈርዖንና ሰራዊቱ በአኺራ እንደሚቀጡ ሁሉ በዱንያም እንደተቀጡ፤
9. ፈርዖን ሰልሞ ነው የሞተው የሚሉ ሰዎች የተሳሳቱ እንደሆነ፤
10. አላህ አያሌ ታዐምራት እንዳሉት፤
11. አላህ ማንንም ቅንጣት ያህል እንኳን እንደማይበድል፤
12. ሰው ምንም አቅም የሌለው ወንጀልም ሲፈፅም ተገዶ እንጂ በፍላጎቱ አይደለም የሚሉትን ሰዎች ስህተት ማጋለጥ፤

13. ታላቁ ነብዩ (ﷺ) የአላህ አገልጋይና ትዕዛዝ የሚሰጣቸው መሆኑን፤
14. አማኞች አሸናፊዎች እንደሆኑ በማብሰር ማጠናከር፤
15. ከሐዲያንን እንደሚሸነፉ አስቀድሞ በመንገር ማስፈራራት፤
16. ከሐዲያን ዕጥፍ ድርብ ቅጣት እንደሚቀጣቸው፤
17. ድል በቁጥር ብዛትና በሃይል ጥንካሬ ብቻ እንደማይገኝ፤
18. አማኝና ከሃዲ ሁልጊዜም ተቃራኒዎች እንደሆኑ፤
19. አላህ ለመልካምና ለመጥፎ ነገሮች ትክክለኛ መገለጫዎች እንዳስቀመጠላቸው፤
20. አላህ ባሪያዎቹን በተለያዩ ነገሮች እንደሚፈትን፤
21. አላህ ባሪያዎቹን ለመፈተን ሲል የተለያዩ ውብ ነገሮችን የሰው ልጅን ስሜት በሚማርክ መልኩ መፍጠሩን፤
22. የአኼራ ሕይወት በጣም ብዙ ነው ብለን ከምናስበው ከዱንያ ሀብትና ጥቅም ጋር ሲነፃፀር እጅግ የበለጠ መሆኑን፤
23. የዱንያ ጥቅም ብዙውን ጊዜ በአመፀኞች እጅ የሚገባ መሆኑንና አኼራዊውን ተድላ ግን ሙዕሚኖች ብቻ እንደሚያገኙት፤
24. አላህን መፍራት ለጀነት ዋስትና እንደሆነ፤
25. ጎህ ሊወጣ ሲቃረብ (በሌሊት ማብቂያ ላይ) የአላህን ምህረት መለመን በኢስላም ተፈላጊ ዒባዳ እንደሆነ፤
26. ሙስሊሞች በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው ሊላበሷቸው የሚገቡ ባህሪያት ምን መምሰል እንዳለባቸው፤
27. ግፍና ክህደት በዱንያም ለአደጋ በአኼራም ለቅጣት ዋነኛ ምክንያት እንደሚሆን፤
28. ሽርክ መልካም ስራን በማጥፋት የአኼራን ሕይወት ዘግናኝ በሆነ ቅጣት ውስጥ ዘወታሪ እንደሚያደርግ፤
29. የአላህን እርዳታና እንክብካቤ የተቸረውን ሰው ማንም ሰው ሊያሸንፈው እንደማይችል፤
30. በአላህ ሕግጋት አለመዳኘት እምነትን የሚያፈርስ ከፍተኛ ወንጀል እንደሆነ፤
31. ያለ እውቀት የሚነገሩ እና አዳዲስ ፈጠራዎች እምነትን ተገን በማድረግ ከሚሰሩ ቅጥፈቶች ዋነኛዎቹ መሆናቸውን፤
32. ሰዎችን ለማግባባት ተብሎ እንኳን ቢሆን በሃይማኖት ላይ ውሸትን ጨምሮ መናገር አደገኛ ወንጀል መሆኑን፤
33. ስለ ቂያማ ቀን እያወሱ መነጋገር እምነት ለመጨመር፤ ወደ መልካም ስራዎች ጉጉት ለማሳደር የሚያስችል መሆኑን፤
34. ካፊሮችን (ከሓዲያንን) ወዳጅ ማድረግ ለሙስሊሞች የማይጠቅም መሆኑን፤
35. ሙዕሚኖችን ቸል ብሎ ከከሓዲያን ጋር ወዳጅነትን መመስረትና ማጥበቅ ከእምነት ጎዳና እንደሚያወጣ፤
36. የሙዕሚኖች ኃይል ደካማ በሆነበት ሀገር የሚኖር ራሱን ከጥቃት ለመከላከል ራሱን ደብቆ መኖር እንደሚፈቀድለት፤
37. የቂያማ ዕለትን ቅጣት በመገንዘብ ለዚያ የፍርድና የምርመራ ቀን ራስን በእምነትና በዒባዳ ማዘጋጀት የግድ መሆኑን፤
38. የሙዕሚኖች ሀይል ደካማ በሆነበት ሀገር ለህይወቱ አስጊ ሁኔታ ውስጥ የሚያስገባው ከሆነ በልቡ ሳይሆን በምላሱ የክህደት ቃል እስከመናገር ቢደርስም አላህ እንደሚምረው ቃል የገባለት መሆኑን እንማራለን።

قُلۡ إِن كُنتُمۡ تُحِبُّونَ ٱللَّهَ فَٱتَّبِعُونِي يُحۡبِبۡكُمُ ٱللَّهُ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ
رَّحِيمٞ ﴿٣١﴾ قُلۡ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَۖ فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَإِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿٣٢﴾

**31-32.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)፡- አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ እኔን ተከተሉኝ። አላህ ይወዳችኋልና። ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምራልና። አላህ መሀሪ አዛኝ ነውና በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)፡- አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ። ብትሸሹም (ቢሸሹ) አላህ ከሓዲያንን አይወድም በላቸው።

**ከዒምራን ቤተሰቦች (31) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁዶች እኛ የአላህ ወዳጆች እና ልጆቹ ነን በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ።)**

۞ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰٓ ءَادَمَ وَنُوحٗا وَءَالَ إِبۡرَٰهِيمَ وَءَالَ عِمۡرَٰنَ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٣٣﴾
ذُرِّيَّةَۢ بَعۡضُهَا مِنۢ بَعۡضٖۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٣٤﴾

**33-34.** አላህ ነብዩ አደምን፤ ነብዩ ኑህን፤ የነብዩ ኢብራሂምን ቤተሰብ እና የነብዩ ዒምራንን ቤተሰብ፤ በየዘመናቸው ከነበሩት ህዝቦች አበለጣቸው (መረጣቸው)። እኒህ ቤተሰቦች ከፊሉ ከከፊሉ የሆነ ዝርያ አድርጎ መረጣቸው። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነው።

إِذۡ قَالَتِ ٱمۡرَأَتُ عِمۡرَٰنَ رَبِّ إِنِّي نَذَرۡتُ لَكَ مَا فِي بَطۡنِي مُحَرَّرٗا فَتَقَبَّلۡ مِنِّيٓۖ إِنَّكَ أَنتَ
ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٣٥﴾ فَلَمَّا وَضَعَتۡهَا قَالَتۡ رَبِّ إِنِّي وَضَعۡتُهَآ أُنثَىٰ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا وَضَعَتۡ
وَلَيۡسَ ٱلذَّكَرُ كَٱلۡأُنثَىٰۖ وَإِنِّي سَمَّيۡتُهَا مَرۡيَمَ وَإِنِّيٓ أُعِيذُهَا بِكَ وَذُرِّيَّتَهَا مِنَ ٱلشَّيۡطَٰنِ
ٱلرَّجِيمِ ﴿٣٦﴾ فَتَقَبَّلَهَا رَبُّهَا بِقَبُولٍ حَسَنٖ وَأَنۢبَتَهَا نَبَاتًا حَسَنٗا وَكَفَّلَهَا زَكَرِيَّاۖ كُلَّمَا دَخَلَ
عَلَيۡهَا زَكَرِيَّا ٱلۡمِحۡرَابَ وَجَدَ عِندَهَا رِزۡقٗاۖ قَالَ يَٰمَرۡيَمُ أَنَّىٰ لَكِ هَٰذَاۖ قَالَتۡ هُوَ مِنۡ عِندِ
ٱللَّهِۖ إِنَّ ٱللَّهَ يَرۡزُقُ مَن يَشَآءُ بِغَيۡرِ حِسَابٍ ﴿٣٧﴾

**35-37.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዒምራን ባለቤት (ሀና) ጌታዬ ሆይ! በሆዴ ውስጥ ያለውን ፅንስ ከሥራ ነፃ የተደረገ ሲሆን ለአንተ አገልግሎት ይውል ዘንድ ተሳልኩ። እናም ተቀበለኝ። አንተ ሰሚና ዐዋቂ ነህና ባለች ጊዜ (የሆነውን አስታውሱ) በላቸው። በወለደቻትም ጊዜ፡- ጌታዬ ሆይ! እኔ ሴት ሆና ወለድኳት አለች። አላህ የወለደችውን ምንነት አዋቂ ነው።

የተመኘችው ወንድ እንደ ወለደቻት ሴት የሚሆን አልነበረም። መርየምም ብዬ ስም አወጣሁላት። እኔም እርሷንና ዝርያዋን ከተረገመው ሰይጣን ተንኮል በአንተ እጠብቃቸዋለሁ አለች። ጌታዬ ሆይ! መርየምን በመልካም አቀባበል ተቀበላት። በመልካም አስተዳደግም አፋፋት። ከዚያም ዘከርያ አሳደጋት። ዘከርያም ወደ ምኩራቧ በገባ ቁጥር እርሷ ዘንድ ሲሳይን አገኘ። መርየም ሆይ! ይህ ለአንቺ ከየት ነው የሚመጣልሽ? አላት። እርሱ የሚመጣልኝ ከአላህ ዘንድ ነው። አላህ እኮ ለሚሻው ሰው ሁሉ ሲሳዩን ያለ ግምት ይሰጣል አለችው።

هُنَالِكَ دَعَا زَكَرِيَّا رَبَّهُۥۖ قَالَ رَبِّ هَبۡ لِي مِن لَّدُنكَ ذُرِّيَّةٗ طَيِّبَةًۖ إِنَّكَ سَمِيعُ ٱلدُّعَآءِ ٣٨ فَنَادَتۡهُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَهُوَ قَآئِمٞ يُصَلِّي فِي ٱلۡمِحۡرَابِ أَنَّ ٱللَّهَ يُبَشِّرُكَ بِيَحۡيَىٰ مُصَدِّقَۢا بِكَلِمَةٖ مِّنَ ٱللَّهِ وَسَيِّدٗا وَحَصُورٗا وَنَبِيّٗا مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ٣٩ قَالَ رَبِّ أَنَّىٰ يَكُونُ لِي غُلَٰمٞ وَقَدۡ بَلَغَنِيَ ٱلۡكِبَرُ وَٱمۡرَأَتِي عَاقِرٞۖ قَالَ كَذَٰلِكَ ٱللَّهُ يَفۡعَلُ مَا يَشَآءُ ٤٠ قَالَ رَبِّ ٱجۡعَل لِّيٓ ءَايَةٗۖ قَالَ ءَايَتُكَ أَلَّا تُكَلِّمَ ٱلنَّاسَ ثَلَٰثَةَ أَيَّامٍ إِلَّا رَمۡزٗاۗ وَٱذۡكُر رَّبَّكَ كَثِيرٗا وَسَبِّحۡ بِٱلۡعَشِيِّ وَٱلۡإِبۡكَٰرِ ٤١

**38-41.** እዚያ ዘንድም ዘከርያ ጌታውን እንደዚህ በማለት ለመነ። ጌታዬ ሆይ!ከአንተ ዘንድ መልካም ዘርን ለእኔ ስጠኝ። አንተ ፀሎትን ሰሚ ነህና አለ። እርሱም በዱዓ (በፆሎት) ማድረጊያ ክፍል ቆሞ ዱዓ ሲያደርግ መላዕክት እንደዚህ ብሎ አላህ በነብዩ የህያ ከአላህ በሆነ ቃል በተወለደው በነብዩ ዒሳም የሚያረጋግጥ ምርጥ፤ ስሜቱን የሚቆጣጠር ከደጋጎቹም አንዱ ሲሆን ያበስርሃል (በማለት መላዕክት አናገረው) ዘከርያም ጌታዬ ሆይ! እኔ እርጅና በእርግጥ ሚስቴም መካን ስትሆን እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለ። መልአኩም ልክ እንደዚሁ ሆናችሁ ነው የምትወልዱት። አላህ የሚሻውን ነገር ሁሉ ይሰራልና አለው። ዘከርያም ጌታዬ ሆይ! ለኔ (ለእዚህ ነገር) ምልክትን አድርግልኝ አለ። ምልክትህ ሶስት ቀን በጥቅሻ እንጂ ሰዎችን አለማናገርህ ነው። በዚያ ጊዜ ጌታህን በብዙ አውሳ። በማታና በጠዋትም አወድሰው አለው።

وَإِذۡ قَالَتِ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَٰمَرۡيَمُ إِنَّ ٱللَّهَ ٱصۡطَفَىٰكِ وَطَهَّرَكِ وَٱصۡطَفَىٰكِ عَلَىٰ نِسَآءِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٤٢ يَٰمَرۡيَمُ ٱقۡنُتِي لِرَبِّكِ وَٱسۡجُدِي وَٱرۡكَعِي مَعَ ٱلرَّٰكِعِينَ ٤٣

**42-43.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መላአክትም መርየም ሆይ! አላህ በእርግጥ መረጠሽ ከነውሮች ሁሉ አነጻሽ። ከዓለማት ሴቶችም መካከል (ያለ ወንድ በመውለድ) መረጠሽ። መርየም ሆይ! ለጌታሽ ታዘዢ። ስገጂም ከሰጋጆች ጋርም ሁነሽ ስገጂ ያለበትን ታሪክ ለህዝቦችህ አውሳ።

ذَٰلِكَ مِنۡ أَنۢبَآءِ ٱلۡغَيۡبِ نُوحِيهِ إِلَيۡكَۚ وَمَا كُنتَ لَدَيۡهِمۡ إِذۡ يُلۡقُونَ أَقۡلَٰمَهُمۡ
أَيُّهُمۡ يَكۡفُلُ مَرۡيَمَ وَمَا كُنتَ لَدَيۡهِمۡ إِذۡ يَخۡتَصِمُونَ ﴿٤٤﴾

**44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ ታሪክ ወደ አንተ ከምናወርደው ከሩቅ ወሬ (ከፊሉ) ነው። መርየምን ማን እንደሚያሳድግ ብዕሮቻቸውን ለዕጣ በጣሉ ጊዜ አንተ እነርሱ ዘንድ አልነበርክም። በሚከራከሩም ጊዜ እነርሱ ዘንድ አልነበርክም።

إِذۡ قَالَتِ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَٰمَرۡيَمُ إِنَّ ٱللَّهَ يُبَشِّرُكِ بِكَلِمَةٖ مِّنۡهُ ٱسۡمُهُ ٱلۡمَسِيحُ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ
وَجِيهٗا فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ وَمِنَ ٱلۡمُقَرَّبِينَ ﴿٤٥﴾ وَيُكَلِّمُ ٱلنَّاسَ فِي ٱلۡمَهۡدِ وَكَهۡلٗا وَمِنَ
ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٤٦﴾ قَالَتۡ رَبِّ أَنَّىٰ يَكُونُ لِي وَلَدٞ وَلَمۡ يَمۡسَسۡنِي بَشَرٞۖ قَالَ كَذَٰلِكِ ٱللَّهُ يَخۡلُقُ
مَا يَشَآءُۚ إِذَا قَضَىٰٓ أَمۡرٗا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٤٧﴾ وَيُعَلِّمُهُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ
وَٱلتَّوۡرَىٰةَ وَٱلۡإِنجِيلَ ﴿٤٨﴾

**45-48.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መላዕክት መርየም ሆይ!አላህ ከርሱ በሆነው ቃል ብቻ የሚፈጠር ስሙ አል መሲህ ዒሳ የመርየም ልጅ በሚባል፤ በዚህ ዓለምም ሆነ በመጨረሻው ዓለም የተከበረና ከባለሟሎቹ አንዱ በሆነ ልጅ ያበስርሻል (ባላት ጊዜ አስታውስ) እርሱም ገና በህፃንነቱ✱ ካደገም በኋላ ሰዎችን ያነጋግራል። ከመልካሞቹም ሰዎች አንዱ ነው (አላት) እርሷም ጌታዬ ሆይ! ማንም ሰው ሳይነካኝ እንዴት ልጅ ይኖረኛል? አለች። (መልአኩ ጅብሪልም) ልክ እነደዚህ ሁነሽ ነው የምትወልጂው ብሎሻል አላት። አላህ የሚሻውን ሁሉ እንደፈለገው ይፈጥራል። ምክንያቱም የአንድን ነገር መሆን በፈለገ ጊዜ የሚለው ሁን ብቻ ነው። ወዲያውኑም ያ ነገር ይሆናል አላት። ጽሕፈትንና ጥበብን፤ ተውራትንና ኢንጂልንም ያስተምረዋል።

✱ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «በሕፃንነት እድሜ ላይ ሳለ ከሶስት ሰዎች በስተቀር የተናገረ የለም። እነርሱም፦

1. ነብዩ ዒሳ (ﷺ)
2. በእስራኤላውያን ልጆች ውስጥ አንድ ጁረይጅ የተባለ ሰው ነበር። ይህ ሰው እየሰገደ ሳለ እናቱ ወደ ርሱ መጥታ ጠራችው። «ጥሪዋን አቤት ልበልን ወይስ ልስገድ?» አለ። እሷም «አላህ ሆይ! የሴሰኛ ሴቶችን ፊት ሳታሳየው አትግደለው። አለች። አንድ ወቅት መስገጃ ቦታው ላይ ሳለ አንዲት ሴት ፊት ለፊቱ ላይ ተጋፍጣ አናገረችው። ነገር ግን እሱ ሊያናግራት ፈቃደኛ አልሆነም። ሴትየዋም ወደ አንድ የከብት እረኛ ሄዳ ሕጋዊ ያልሆነ ግብረ. ስጋ ግንኙነት ፈፅማ አንድ ወንድ ልጅ ወለደች። «ይህ ልጅ የጁረይጅ ነው» ብላ ለሰዎች ተናገረች። ሰዎችም ወደ ጁረይጅ

በመምጣት መስገጃ ቦታውን አፈራረሱ። ከመስገጃው ቦታውም አስወጥተው ዘለፉት። ጁረይጅ ውዱዕ አድርጎ ከሰገደ በኋላ ወደ ልጁ መጥቶ «አንተ ልጅ! አባትህ ማነው?» ሲል ጠየቀው። ሕፃኑም «የከብቶቹ እረኛ ነው» ሲል መለሰ። ሰዎች ይህን ከሰሙ በኋላ መስገጃህን ከወርቅ እንስራልህ» አሉት። እሱ ግን «ከጭቃ በስተቀር ከምንም አትስሩት» አላቸው።

3. ከእስራኢላዊያን ልጆች መካከል የሆነች አንዲት ሴት ልጇን እያጠባች ሳለ በጣም መለሎ የሆነ ሰው ፈረስ እየጋለበ በአጠገቧ አለፈ። እሷም «አላህ ሆይ! ልጄን እንደሱ አድርገው» አለች። ህፃኑም ጡቶቿን ከአፉ አወጣና ወደ ፈረሰኛው እየተመለከተ «አላህ ሆይ! እንደሱ አታደርገኝ» አለና ጡቶቿን ዳግመኛ በመጉረስ መጥባቱ ቀጠለ። አቡ ሁረይራህ ሲናሩ «የአላህ መልዕክተኛ ጣታቸውን እየጠቡ እመለከታቸዋለሁ» ጥቂት እንደቆየ አንዲት ሴት ባሪያ በአጠገቧ አለፈች። ይህች ሴትም «አላህ ሆይ! ልጄን እንደዚህች ሴት አታድረገው» አለች። ሕፃኑም ጡቶቿን መጥባቱን ትቶ ወደ ባሪያዋ ሴት እየተመለከተ «አላህ ሆይ! እንደሷ አድርገኝ» አለና መጥባቱን ቀጠለ። ሴትዮዋም ለምን? ብላ ስትጠየቅ ሕፃኑም እንዲህ ሲል መለሰላት። «ፈረሰኛው ሰው በምድር ላይ ካሉት ጨቋኞች መካከል አንዱ ነው። ሰዎች ይህችን ባሪያ ሴት ሰርቃለች፤ ዝሙት ፈፅመላች ይሏታል። ነገር ግን ምንም አልፈፀመችም።»

وَرَسُولًا إِلَىٰ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ أَنِّي قَدۡ جِئۡتُكُم بِـَٔايَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ أَنِّيٓ أَخۡلُقُ لَكُم مِّنَ ٱلطِّينِ كَهَيۡـَٔةِ ٱلطَّيۡرِ فَأَنفُخُ فِيهِ فَيَكُونُ طَيۡرَۢا بِإِذۡنِ ٱللَّهِۖ وَأُبۡرِئُ ٱلۡأَكۡمَهَ وَٱلۡأَبۡرَصَ وَأُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰ بِإِذۡنِ ٱللَّهِۖ وَأُنَبِّئُكُم بِمَا تَأۡكُلُونَ وَمَا تَدَّخِرُونَ فِي بُيُوتِكُمۡۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لَّكُمۡ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ﴿٤٩﴾ وَمُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيَّ مِنَ ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَلِأُحِلَّ لَكُم بَعۡضَ ٱلَّذِي حُرِّمَ عَلَيۡكُمۡۚ وَجِئۡتُكُم بِـَٔايَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ﴿٥٠﴾ إِنَّ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ﴿٥١﴾

**49-51.** ወደ ኢስራኢል ልጆችም መልዕክተኛ ያደርገዋል። ከዚያ እኔ ከጌታዬ ዘንድ በእርግጥ በተዐምር መጣሁላችሁ። እኔ ለእናንተ ከጭቃ የወፍ ቅርፅ አይነት እፈጥራለሁ። በእርሱም እተነፍስበታለሁ። ከዚያም በአላህ ፈቃድ ወፍ ይሆናል። እውር ሆኖ የተወለደን ለምጻኛንም በአላህ ፈቃድ አድናለሁ። ሙታንንም (በአላህ ፈቃድ) አስነሳለሁ። የምትበሉትንና በየቤታችሁ የምታደልቡትን ሁሉ እነግራችኋለሁ። መረጃዎችን አገናዝባችሁ የምታምኑ እንደሆናችሁ ለእናንተ በዚህ ውስጥ ለነብይነት ግልፅ ተዐምር አለበት። ከእኔ በፊት የነበረውን ተውራትን ያረጋገጥኩ ስሆን ያንም በእናንተ ላይ እርም የተደረገውን ነገር ከፊሉን ለእናንተ እፈቅድ ዘንድ መጣሁላችሁ። ከጌታችሁም በሆነ ተዐምር መጣሁላችሁ። አላህን ፍሩ። እኔንም ታዘዙኝ። አላህ ጌታየና የእናንተም ጌታችሁ ነው። ስለዚህ በብቸኝነት ተገዙት። ይህ ቀጥተኛው መንገድ ነው አላቸው።

﴿۞فَلَمَّآ أَحَسَّ عِيسَىٰ مِنۡهُمُ ٱلۡكُفۡرَ قَالَ مَنۡ أَنصَارِيٓ إِلَى ٱللَّهِۖ قَالَ ٱلۡحَوَارِيُّونَ نَحۡنُ
أَنصَارُ ٱللَّهِ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَٱشۡهَدۡ بِأَنَّا مُسۡلِمُونَ ٥٢ رَبَّنَآ ءَامَنَّا بِمَآ أَنزَلۡتَ وَٱتَّبَعۡنَا ٱلرَّسُولَ
فَٱكۡتُبۡنَا مَعَ ٱلشَّٰهِدِينَ ٥٣﴾

**52-53.** ዒሳ ከእነርሱ ክህደት በተሰማው ጊዜ:- ወደ አላህ ተጨምረው የእኔ ረዳቶች የሚሆኑ እነማን ናቸው? አለ። ሀዋርያት:- ዒሳ ሆይ!እኛ የአላህ ረዳቶች ነን። በአላህ አምነናል። እኛም ትክክለኛና ታዛዦች መሆናችንን መስክር አሉ። ጌታችን ሆይ! ባወረድከው አመንን መልዕክተኛውን ተከተለናል። እኛም (በአንተ ብቸኛ አምላክነት በነብያት መልዕክተኛነት) ከመስካሪዎች ጋራ መዝግበን አሉ።

﴿وَمَكَرُواْ وَمَكَرَ ٱللَّهُۖ وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلۡمَٰكِرِينَ ٥٤﴾

**54.** (አይሁዶችም) በዒሳ ላይ አደሙ። አላህ ግን አድማቸውን አከሸፈባቸው። አላህ ከአድመኞች* ሁሉ በላጭ ነውና። አላህ የአድመኞችን ሴራ በማክሸፍ ከሁሉ የበለጠ ነውና።

* እዚህ ላይ ከአላህ ባህሪያት መካከል አንዱ መክር (ማሴር) የተባለው መሆኑን ያመለክታል። ባይሆን የእሱ ሴራና የሰው ልጅ ሴራ የተለየና የማይመሳሰል መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል። ከአላህ አንጻር ሲታይ ለርሱ ሙሉ ባህሪና ለጠላቶች የሚያድም መሆኑን ያመላክታል የዚሁ አባባል ተመሳሳዩ አልፏልና ልብ ይበሉ።

﴿إِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَىٰٓ إِنِّي مُتَوَفِّيكَ وَرَافِعُكَ إِلَيَّ وَمُطَهِّرُكَ مِنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَجَاعِلُ ٱلَّذِينَ
ٱتَّبَعُوكَ فَوۡقَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِۖ ثُمَّ إِلَيَّ مَرۡجِعُكُمۡ فَأَحۡكُمُ بَيۡنَكُمۡ فِيمَا
كُنتُمۡ فِيهِ تَخۡتَلِفُونَ ٥٥ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فَأُعَذِّبُهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدٗا فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ
وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ٥٦ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَيُوَفِّيهِمۡ أُجُورَهُمۡۗ
وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ ٥٧﴾

**55-57.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ:- ዒሳ ሆይ! ወደ እኔ ወሳጅህና ከምድር ወደ ላይ አንሽህ ነኝ።*1 ከነዚያም በእኔ ከካዱት ሰዎች (ተንኮል) አጥሪህ ነኝ። እነዚያን የተከተሉህን ሰዎችንም እስከ ትንሳኤ ቀን*2 ድረስ ከነዚያ ከካዱት ሰዎች በላይ አድራጊ ነኝ። ከዚያ የሁላችሁም መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው። ያን ትለያዩበት በነበራችሁበት ነገርም በመካከላችሁ እፈርዳለሁ ባለ

ጊዜ (የነበረውን ሁኔታ ለህዝቦችህ አውሳላቸው)። እነዚያ (ዒሳን በመቃወም ወይም በማግነን) በአላህ መመሪያዎች የካዱ ሰዎች በቅርቢቱ ዓለምም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ብርቱ ቅጣትን እቀጣቸዋለሁ። ለእነርሱም ምንም ረዳቶች የሏቸውም። እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞች ያመኑና መልካም ስራዎችን የሰሩ ሰዎች ሁሉ አላህ ምንዳቸውን ይሞላላቸዋል። አላህም በክህደታቸው በዳዮችን አይወድምና።

✶1 ወሳጅህ እንደማለት ነው። ይህ አባባል የአላህን ከፍጥረታት በላይ መሆን ከሚያስረዱት አናቅፅ አንዱ ነው። አንኒሳእ (1) (78) ኛው፤ አል. አንዓም (18) ኛው፤ አንነህል (102) ኛው፤ ፋጢር (10) ኛው፤ አስሰጀደህ (5) ኛው፤ አልመዓሪጅ (4) ኛው አንቀፅም ይህንኑ እውነታ ማለትም የአላህን የበላይነት ከሚያስረዱት አናቅፅ ከፊሎቹ ናቸው።

✶2 (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ (ዒሳ የመርየም ልጅ በእናንተ መካከል በእርግጥ በፍትህ መሪ ሆኖ ይነሳል። መስቀልን ይሰብራል። አሳማን ይገድላል። ጅዝያ መክፈልም አይኖርም። የሚቀበል እስከማይኖር ድረስ ገንዘብ ይበረከታል። አንዲት ለአላህ ተብላ የምትደረግ ስግደት፤ በዚህች ምድር ላይ ከሚገኙ ነገሮች በላይ ትሆናለች» አቡ ሁረይራህ እንዲህ በማለት ሐዲሱ ላይ በዘገባቸው አክለዋል። «ይህን ለማወቅ ካሻችሁ «ከመፅሐፉ ሰዎች ከመሞቱ በፊት በርሱ (በዒሳ) በእርግጥ የሚያምን እንጂ አንድም የለም። በትንሳኤም ቀንም በነርሱ ላይ መስካሪ ይሆናል» (አን-ኒሳእ፡ 159) የሚለውን አንብቡ።»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «የመርየም ልጅ ዒሳ በመካከላችሁ ቢነሳ ምን ልትሆኑ ነው? እሱ ዒሳ በቁርኣን ሕግጋት መሰረት ይዳኛል እንጂ በኢንጂል አይዳኝም።»

ذَٰلِكَ نَتۡلُوهُ عَلَيۡكَ مِنَ ٱلۡأٓيَٰتِ وَٱلذِّكۡرِ ٱلۡحَكِيمِ ٥٨

58. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ የዒሳ ነብይነት ታሪክ ከተዐምራቶችና ጥበብን ከያዘው ተግሳፅ ጥቂት አካል ሲሆን በእናንተ ላይ እናነበዋለን።

إِنَّ مَثَلَ عِيسَىٰ عِندَ ٱللَّهِ كَمَثَلِ ءَادَمَۖ خَلَقَهُۥ مِن تُرَابٖ ثُمَّ قَالَ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ٥٩
ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡمُمۡتَرِينَ ٦٠

59-60. አላህ ዘንድ የዒሳ (ያለ አባት መፈጠር መወለድ) ምሳሌ ልክ ያለ አባትና ያለ እናት እንደተፈጠሩት አባታችን አደም ቢጤ ነው። አላህ አደምን ከአፈር ፈጠረውና ከዚያም ሰው ሁን አለው። ከዚያም ሰው ሆነ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዒሳ ጉዳይ ትክክለኛው ታሪክ ከጌታህ ዘንድ የመጣልህ እውነት ብቻ ነው። እናም በእውነቱ ከተጠራጣሪዎች አትሁን።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከ (58-59) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የነጅራን የሉዑካን ቡድን ወደ ነቢዩ በመምጣት ነብዩ ዒሳን የአላህ አገልጋይና ባሪያ እያሉ ስለመጥራታቸው ጠየቁ። «(ለምን ነብዩ ዒሳን የአላህ አገልጋይ እያልክ ትጠራዋለህ)» በማለት ተቃውሞ ሲያሰሙ ነብዩ (ይህ አቋማቸው የፈጣሪ አቋም መሆኑን በመጠቆም በአቋማቸው ላይ ይፀናሉ። እነዚህ የነጂራን ሉዕካን በጣም በመቆጣት «(እስኪ ከእሱ ሌላ ያለ አባት የተፈጠረ አንድ አካል ወይም ሰው ጠቁሙን)» በማለት ሲጠይቋቸው እነዚህ የቁርኣን አናቅፅ ወረዱ። (ዋሒዲና ሱዩጢ)

فَمَنْ حَآجَّكَ فِيهِ مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَكَ مِنَ ٱلْعِلْمِ فَقُلْ تَعَالَوْا۟ نَدْعُ أَبْنَآءَنَا وَأَبْنَآءَكُمْ
وَنِسَآءَنَا وَنِسَآءَكُمْ وَأَنفُسَنَا وَأَنفُسَكُمْ ثُمَّ نَبْتَهِلْ فَنَجْعَل لَّعْنَتَ ٱللَّهِ عَلَى ٱلْكَٰذِبِينَ ٦١
إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ ٱلْقَصَصُ ٱلْحَقُّ ۚ وَمَا مِنْ إِلَٰهٍ إِلَّا ٱللَّهُ ۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ٦٢
فَإِن تَوَلَّوْا۟ فَإِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌۢ بِٱلْمُفْسِدِينَ ٦٣

**61-63.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እውቀት ከመጣልህ በኋላ (በርሱ) በዒሳ የተከራከሩህን ሰዎች ኑ ልጆቻችንንና ልጆቻችሁን፤ ሴቶቻችንንና (ሚስቶቻችንና) ሴቶቻችሁን (ሚስቶቻችሁን) ነፍሶቻችንንና ነፍሶቻችሁን እንጥራና ከዚያ አጥብቀን አላህን እንለምን። የአላህንም ቁጣ በውሸታሞች ላይ እናድርግ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ ስለ ዒሳ የነገርኩህ እውነተኛ ታሪክ ነው። ትክክለኛ አምላክም ከአላህ በስተቀር ማንም የለም። አላህ እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ አምላክ ነው። እናም (ከማመን) እምቢ ቢሉ አጥፊዎች እነርሱ ብቻ ናቸው። አላህ አጥፊዎቹን (ከደህናዎቹ) ለይቶ አዋቂ ነው።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (61) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሁለት የአንሷር ምሁሮች ከነጅራን ወደ ነብዩ (ﷺ) በመቅረብ በሚያነጋግሯቸው ጊዜ ነብዩ (ﷺ) (ይልቁንስ ለምን አትሰልሙም አሏቸው) እነሱም (ከእናንተ በፊት ነው የሰለምነው ይላሉ) ነብዩም (ﷺ) (ዋሻችሁ ከመስለም የከለከላችሁ አላህ ልጅ አለው ማለታችሁ፤ መስቀልን ማምለካችሁ እና ከርከሮ እና አሳማ መመገባችሁ ነው አሏቸው። የአንሷር ምሁራኑም ዒሳ የአላህ ልጅ ካልሆነ አባቱ ማን ነው በማለት ጠየቁ። ነብዩ (ﷺ) ሁልጊዜም መልስ ለመስጠት አይቸኩሉም ነበርና ዝም ባሉበት ይህ የቁርኣን አንቀፅ ወረደ። በማስከተልም ነብዩ (ﷺ) ልጆቻቸውን ማለትም ፋጡማን ከነ ልጆቻቸው ከሀሰንና ከሁሴይን ጋር በመሰብሰብ እነርሱም ዘመዶቻቸውን እንዲጠሩና እንዲረጋገሙ ወይም ግብር እንዲከፍሉ ሲጠይቋቸው መረጋገሙን ፈሩ። ሀሰት ላይ መሆናቸውን ያውቃሉና ግብር ለመክፈል ተስማሙ። ነብዩ ግብሩን የተቀበሉ መሆናቸውን የታሪክ መፅሐፎች ዘግበዋል። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

قُلۡ يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ تَعَالَوۡاْ إِلَىٰ كَلِمَةٖ سَوَآءِۭ بَيۡنَنَا وَبَيۡنَكُمۡ أَلَّا نَعۡبُدَ إِلَّا ٱللَّهَ وَلَا نُشۡرِكَ
بِهِۦ شَيۡـٔٗا وَلَا يَتَّخِذَ بَعۡضُنَا بَعۡضًا أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِۚ فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَقُولُواْ ٱشۡهَدُواْ بِأَنَّا
مُسۡلِمُونَ ٦٤ يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ لِمَ تُحَآجُّونَ فِيٓ إِبۡرَٰهِيمَ وَمَآ أُنزِلَتِ ٱلتَّوۡرَىٰةُ وَٱلۡإِنجِيلُ
إِلَّا مِنۢ بَعۡدِهِۦٓۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ٦٥ هَٰٓأَنتُمۡ هَٰٓؤُلَآءِ حَٰجَجۡتُمۡ فِيمَا لَكُم بِهِۦ عِلۡمٞ فَلِمَ
تُحَآجُّونَ فِيمَا لَيۡسَ لَكُم بِهِۦ عِلۡمٞۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ وَأَنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ٦٦

**64-66.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመጽሐፍ ባለቤቶች ሆይ!በእኛና በእናንተ መካከል ትክክል ወደ ሆነችው ቃል ኑ። (እርሷም) «አላህን ብቻ እንጂ ሌላን ላንገዛ፤ በእርሱም ምንንም ላናጋራ፤ ከፊላችንም ከፊሉን ከአላህ ሌላ አማልክት አድርጎ ላይዝ» ነው በላቸው። (ሙስሊሞች ሆይ!) እምቢ ካሉም እኛ ሙስሊሞች መሆናችንን መስክሩ በሏቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ሆይ! በኢብራሂም (ዙሪያ) ለምን ትከራከራላችሁ። ተውራትና ኢንጂል ከእርሱ በኋላ እንጂ አልተወረዱም። ልብ አታደርጉምን? በላቸው። (ሙስሊሞች ሆይ!) ንቁ! እናንተ እነዚያ ለእናንተ በርሱ እውቀት ባላችሁ ነገር የተከራከራችሁ ናችሁ። ታዲያ እውቀት በሌላችሁ ነገር ላይ ለምን ትከራከራላችሁ? አላህ ሁሉን ነገር ያውቃል። እናንተ ግን አታውቁም።

ከዒምራን ቤተሰቦች (65) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የነጅራን ነሷራ እና የአይሁድ ምሁራን ነብዩ (ﷺ) አጠገብ ተሰባስበው አይሁዶች ኢብራሂም የሁዲ ነበር ሲሉ ክርስቲያኖች ደግሞ ኢብራሂም ክርስቲያን ነበር በማለታቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ እና ኢብኑ ከሲር)

مَا كَانَ إِبۡرَٰهِيمُ يَهُودِيّٗا وَلَا نَصۡرَانِيّٗا وَلَٰكِن كَانَ حَنِيفٗا مُّسۡلِمٗا وَمَا كَانَ مِنَ
ٱلۡمُشۡرِكِينَ ٦٧ إِنَّ أَوۡلَى ٱلنَّاسِ بِإِبۡرَٰهِيمَ لَلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُ وَهَٰذَا ٱلنَّبِيُّ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْۗ
وَٱللَّهُ وَلِيُّ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٦٨

**67-68.** ኢብራሂም አይሁድም ሆነ ክርስቲያንም አልነበረም። ግን ወደ ቀጥተኛው ሃይማኖት የተዘነበለ ቀጥ ያለ ሙስሊም ነበር። ከአጋሪዎችም አልነበረም። ከሰው ሁሉ ኢብራሂምን በመከተል ተገቢዎች እነዚያ በዘመኑ የተከተሉት ሰዎችና፤ ይህ ነብይ (ነብዩ ሙሐመድ) እና እነዚያ በሙሐመድ ያመኑት ሰዎች ብቻ ናቸው። አላህ የትክክለኛ አማኞች ሁሉ ወዳጅ ነው።

وَدَّت طَّآئِفَةٌ مِّنْ أَهْلِ ٱلْكِتَـٰبِ لَوْ يُضِلُّونَكُمْ وَمَا يُضِلُّونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمْ وَمَا يَشْعُرُونَ ﴿٦٩﴾
يَـٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَـٰبِ لِمَ تَكْفُرُونَ بِـَٔايَـٰتِ ٱللَّهِ وَأَنتُمْ تَشْهَدُونَ ﴿٧٠﴾ يَـٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَـٰبِ لِمَ تَلْبِسُونَ
ٱلْحَقَّ بِٱلْبَـٰطِلِ وَتَكْتُمُونَ ٱلْحَقَّ وَأَنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٧١﴾

**69-71.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ከመጽሐፍ ባለቤቶች የተወሰኑት ወገኖች ነፍሶቻቸውን እንጂ የማያሳስቱ ሲሆኑ እናንተን ሊያሳስቷችሁ ተመኙ። እራሳቸውን እንጂ ማንንም አያሳሳስቱም። እነርሱ ግን ይህንን እውነታ አያውቁም። እናንተ የመፅሐፍ ባለቤቶች ሆይ! እናንተ የምታውቁ ስትሆኑ በአላህ አንቀፆች ለምን ትክዳላችሁ? እናንተ የመፅሐፍ ባለቤቶች ሆይ! እውነትን ከውሸት ጋር ለምን ትቀላቅላላችሁ። እውነቱን እናንተ የምታውቁ ስትሆኑ ለምን ትደብቃላችሁ?

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (31-71) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ዱዓ ለሙስሊም መንፈሳዊና ቁሳዊ ሕይወት መዳበር አጅግ ከፍተኛ ሚና እንዳለው፤
2. አላህን ማስታወስ እርሱን ማወደስ የሱብሂንና የአስርን ሶላት ወቅታቸውን ጠብቆ መስገድ ያለውን ምንዳ፤
3. አላህን በሙሉ ልብ መውደድ ግዴታ እንደሆነ፤
4. የእርሱም ውዴታ የሚገለፀው የመልዕክተኛውን የሙሐመድን (ﷺ) አርአያ በመከተል መሆኑን፤
5. የአላህ እና የነብዩን (ﷺ) ትዕዛዝ ሳያከብሩ በምላስ ብቻ አላህን እና ሙሐመድን እወዳለሁ ማለቱ ብቻ ፋይዳ የሌለው መሆኑን፤
6. ነብዩን (ﷺ) መከተል በሁሉም ነገር ግዴታ መሆኑን፤
7. አላህ በራሱ ምርጫ የፈለገውን ያህል ፀጋ ለፈለገው ባሪያ ሊሰጥ እንደሚችል፤
8. ዒሳ ሰዎች እንደሚሉት ጌታ ወይም የአላህ ልጅ ሳይሆኑ ነብይና በእርሱም ምርጫ አገልጋይ ባሪያው መሆናቸውን፤
9. አላህ ለመርየም እናት ለሀና ፀሎቷን ተቀብሎ፤ የተመኘችውን ልጅ የሰጣትና ከነዝርያዋ ከሰይጣን ተንኮል እንደጠበቃቸው፤
10. የእርሱን እርዳታና ጥበቃ ለሚለምኑ ባሮች ሁሉ ተመሳሳይ ውለታን ከማድረግ የማይሰለች ጌታ መሆኑን።
11. ለአላህ ብሎ ስለት መነየት የሚፈቀድ መሆኑን።
12. አንድ ሰው አደርገዋለሁ ብሎ ያቀደውን መልካም ስራ ሳይተገብር ሲያመልጠው መፀፀት እንደሚችል፤
13. አላህ ለተመረጡ የእርሱ አገልጋይ ባሪያዎቹ ልዩ ተዐምራት እንደሚሸልም፤
14. የነብዩ ዒሳ ወላጅ እናት መርየም አላህ የሰጣትን ልዩ ማዕረግና ክብር ከፍተኛነት መሆኑን፤
15. የነብዩ ዒሳ ጉዳይ የተወሳሰበ አይደለም። እጅግ ቀላል ነው። አደምን ያለ ወላጆች ከአፈር፤ ሐዋን ያለ እናት ከአባት ብቻ ያስገኘና ምንም ነገር የማይሳነው አምላክ ዒሳን ያለ አባት የፈጠረ መሆኑን፤
16. የአላህ ነብይ የሆኑት ዒሳ (እየሱስ) ና ወላጅ እናታቸው አላህ ዘንድ ያላቸው ከፍተኛ ማዕረግና ክብር፤

17. ዒሳ አንደበታቸው ባልተፈታበት የህፃንነት እድሜያቸው ወቅት ሊናገሩ እንደቻሉ፤
18. ያላወቁትን ነገር ጠይቆ መረዳት ተገቢ መሆኑን፤
19. አላህ በተለያዩ ወቅቶች ለነበሩ ሕዝቦች እንደ መመሪያ የላካቸው መፅሐፍት የነበራቸው ክብር፤
20. ሒክማ (ጥበብ) ዳዕዋን ለማካሄድም ሆነ ከሰዎች ጋር በሰላም ለመኗኗር አጋዥ የሆነ ጠቃሚ ነገር መሆኑን፤
21. ገይብን (ሩቁን ነገር) ማወቅ የአላህ ስልጣን ብቻ ችሎታ እንደሆነ፤
22. ነብዩ ዒሳ በአላህ ፈቃድ ታላላቅ ተዐምራትን እንዳሳዩ፤
23. ነብዩ ዒሳ የተላኩት የእስራኤል ልጆችን ወደ ትክክለኛው እምነትና ዒባዳ ለመጥራት መሆኑን፤
24. እውነትን አለባብሶ ማለፍ እና አስመስሎ መኖር በኢስላም ፍፁም የተወገዘ መሆኑን፤
25. ከአይሁድና ክርስቲያኖች ብዙዎች የሌት ተቀን ሕልማቸውና ምኞታቸው ሙስሊሞችን ማጥመምና ማሳሳት መሆኑን፤
26. የመጥፎ ነገር መጨረሻው ሰሪውንም ጭምር ለጉዳት እንደሚዳርግ እንማራለን።

وَقَالَت طَّآئِفَةٞ مِّنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ ءَامِنُواْ بِٱلَّذِيٓ أُنزِلَ عَلَى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَجۡهَ ٱلنَّهَارِ وَٱكۡفُرُوٓاْ
ءَاخِرَهُۥ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ٧٢ وَلَا تُؤۡمِنُوٓاْ إِلَّا لِمَن تَبِعَ دِينَكُمۡ قُلۡ إِنَّ ٱلۡهُدَىٰ هُدَى ٱللَّهِ أَن
يُؤۡتَىٰٓ أَحَدٞ مِّثۡلَ مَآ أُوتِيتُمۡ أَوۡ يُحَآجُّوكُمۡ عِندَ رَبِّكُمۡۗ قُلۡ إِنَّ ٱلۡفَضۡلَ بِيَدِ ٱللَّهِ يُؤۡتِيهِ مَن يَشَآءُۗ
وَٱللَّهُ وَٰسِعٌ عَلِيمٞ ٧٣ يَخۡتَصُّ بِرَحۡمَتِهِۦ مَن يَشَآءُۗ وَٱللَّهُ ذُو ٱلۡفَضۡلِ ٱلۡعَظِيمِ ٧٤

**72-74.** ከመፅሐፍ ባለቤቶች የሆኑ ጭፍሮች አሉ በተወረደው ቁርኣን በቀኑ መጀመሪያ ላይ እመኑበትና በቀኑ መጨረሻ ላይ ግን ካዱ። እነርሱ ሊመለሱ ይከጀላልና አሉ። የመፅሐፍ ባለቤቶች! እርስ በራሳቸው ሃይማኖታችሁን ለተከተለ ሰው እንጂ አትመኑ (አትግለፁ) ተባባሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ትክክለኛው መመሪያ የአላህ መመሪያ ብቻ ነው በላቸው። እናንተ ያገኛችሁትን እድል እንዲያገኙ ወይም በእርሱ ከጌታችሁ ፊት እንዳይሞግቷችሁ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ችሮታ በአላህ እጅ ብቻ ነው። ለሚፈልገው ሰው ይሰጠዋል። አላህ ችሮታው ሰፊና ሁሉን አዋቂ ነውና በላቸው። በችሮታው (ለነብይነት) የሚሻውን ይመርጣል። አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (72) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አስራ ሁለት የአይሁድ ሙሁራን ተሰባስበው ጧት ጧት ሙሐመድ እምነቴን የሚለውን ተቀበሉትና ከሰዓት በኋላ አስተባበሉት። ለምን ስትባሉ ስለ አንተ ጉዳይ መፅሐፍትን ስናገላብጥና አዋቂዎችን ስናማክር እውነትነቱን በማጣታችን ነው በሉት። በዚህን ጊዜ በትክክል እምነቱን የተከተሉትን አረቦች ጥርጣሬ ላይ ትጥሏቸዋላችሁ ብለው እርስ በእርሳቸው መመካከራቸውን ለማጋለጥ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

۞ وَمِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ مَنۡ إِن تَأۡمَنۡهُ بِقِنطَارٖ يُؤَدِّهِۦٓ إِلَيۡكَ وَمِنۡهُم مَّنۡ إِن تَأۡمَنۡهُ بِدِينَارٖ
لَّا يُؤَدِّهِۦٓ إِلَيۡكَ إِلَّا مَا دُمۡتَ عَلَيۡهِ قَآئِمٗاۗ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ قَالُواْ لَيۡسَ عَلَيۡنَا فِي ٱلۡأُمِّيِّـۧنَ سَبِيلٞ
وَيَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ﴿٧٥﴾ بَلَىٰۚ مَنۡ أَوۡفَىٰ بِعَهۡدِهِۦ وَٱتَّقَىٰ فَإِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ
ٱلۡمُتَّقِينَ ﴿٧٦﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَشۡتَرُونَ بِعَهۡدِ ٱللَّهِ وَأَيۡمَٰنِهِمۡ ثَمَنٗا قَلِيلًا أُوْلَٰٓئِكَ لَا خَلَٰقَ لَهُمۡ فِي
ٱلۡأٓخِرَةِ وَلَا يُكَلِّمُهُمُ ٱللَّهُ وَلَا يَنظُرُ إِلَيۡهِمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ وَلَا يُزَكِّيهِمۡ وَلَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ ﴿٧٧﴾

**75-77.** ከመጽሐፉ ባለቤቶች መካከል በብዙ ገንዘብ ላይ ታምኖ ቅንጣት ሳያጎድል የሚመልስልህ ሰው አለ። ከእነርሱም መካከል በአንድ ዲናር እንኳን ብታምነው ሁል ጊዜም እሱ ላይ የምትጠባበቅ ካልሆንክ በስተቀር የማይመልስልህ ሰው አለ። ይህ በመሀይማን ህዝቦች ላይ በምናደርገው ግፍ ሁሉ በእኛ ላይ ምንም የምንጠየቅበት መንገድ የለብንም ስለሚሉና እነርሱም እያወቁ በአላህ ላይ ውሸትን ስለሚናገሩ ነው። አይደለም (ተጠያቂነት አለባቸው።) ያ! በቃል ኪዳኑ የሞላና የተጠነቀቀ ሰው ሁሉ አላህ ጥንቁቆችን ይወዳል። እነዚያ በአላህ ቃል ኪዳንና በመሀላዎቻቸው ጥቂትን (እምነት) ዋጋን የሚለውጡ ሰዎች ሁሉ እነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም ምንም እድል የላቸውም። በትንሳኤም ቀን አላህ አያነጋግራቸውም። ወደ እነርሱም አይመለከትም። አያፀዳቸውምም። ከቶውንም ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (77) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ አሽአስ ቢን ቀይስ የተባለ ግለሰብ እንደተናገረው በእኔና በአንድ አይሁድ መካከል የመሬት ክርክር ነበርና ጉዳዩን ወደ ነብዩ (ﷺ) አድርሰነው በመታየት ላይ ሳለ ምስክር አለህ ወይ? በማለት ሲጠይቁኝ የለኝም በማለቴ ታዲያ ይማልልህ አሉኝ። እኔም እሱ ለመሀላ ምን ግድ አለው በውሸትም ቢሆን ይምልና ንብረቴን ይወስደዋል እኮ ስላቸው ነበር ይህ የቁርአን አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَإِنَّ مِنۡهُمۡ لَفَرِيقٗا يَلۡوُۥنَ أَلۡسِنَتَهُم بِٱلۡكِتَٰبِ لِتَحۡسَبُوهُ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ
وَمَا هُوَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَيَقُولُونَ هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ وَمَا هُوَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ
وَيَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ﴿٧٨﴾

**78.** ከእነርሱም መካከል እርሱ ከመጽሐፉ ያልሆነን ነገር ከመጽሐፉ አካል መሆኑን እንድታስቡ በመጽሐፉ ምላሶቻቸውን የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ። እርሱ ከአላህ ዘንድ ያልመጣ (ያልወረደ) ሲሆን ከአላህ ዘንድ ነው የመጣ (የወረደ) ይላሉ። የሚያውቁ ሲሆኑ በአላህ ላይ ውሸትን ይናገራሉ።

مَا كَانَ لِبَشَرٍ أَن يُؤْتِيَهُ ٱللَّهُ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحُكْمَ وَٱلنُّبُوَّةَ ثُمَّ يَقُولَ لِلنَّاسِ كُونُوا۟ عِبَادًا لِّى مِن دُونِ ٱللَّهِ وَلَٰكِن كُونُوا۟ رَبَّٰنِيِّۦنَ بِمَا كُنتُمْ تُعَلِّمُونَ ٱلْكِتَٰبَ وَبِمَا كُنتُمْ تَدْرُسُونَ ﴿٧٩﴾ وَلَا يَأْمُرَكُمْ أَن تَتَّخِذُوا۟ ٱلْمَلَٰٓئِكَةَ وَٱلنَّبِيِّۦنَ أَرْبَابًا ۗ أَيَأْمُرُكُم بِٱلْكُفْرِ بَعْدَ إِذْ أَنتُم مُّسْلِمُونَ ﴿٨٠﴾

**79-80.** አላህ መጽሐፍን ጥበብንና ነብይነትን የሰጠው ማንም ግለሰብ ከዚያ ለሰዎች ከአላህ ሌላ ለእኔ ባሮች ሁኑ ሊል አይገባውም። ይልቁንም መጽሐፍን የምታስተምሩና የምታጠኑ በነበራችሁበት በእውቀታችሁ ለራሳችሁ ተግባሪዎች ሁኑ ይላቸዋል። መላዕክትንና ነብያትንም አማልክት* አድርጋችሁ እንድትይዙ ሊያዛችሁ አይገባም። (እናንተ) ትክክለኛ ሙስሊሞች ከሆናችሁ በኋላ በክህደት ያዛችኋልን?

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «ልክ ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ ዒሳን ድንበር በማለፍ እንዳወደሱት እኔንም ድንበር አልፋችሁ አታወድሱኝ። እኔ ባሪያ እንጂ ሌላ አይደለሁም። ስለዚህ የአላህ ባሪያዉና መልዕክተኛው በሉኝ» (ብለዋል)

وَإِذْ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلنَّبِيِّۦنَ لَمَآ ءَاتَيْتُكُم مِّن كِتَٰبٍ وَحِكْمَةٍ ثُمَّ جَآءَكُمْ رَسُولٌ مُّصَدِّقٌ لِّمَا مَعَكُمْ لَتُؤْمِنُنَّ بِهِۦ وَلَتَنصُرُنَّهُۥ ۚ قَالَ ءَأَقْرَرْتُمْ وَأَخَذْتُمْ عَلَىٰ ذَٰلِكُمْ إِصْرِى ۖ قَالُوٓا۟ أَقْرَرْنَا ۚ قَالَ فَٱشْهَدُوا۟ وَأَنَا۠ مَعَكُم مِّنَ ٱلشَّٰهِدِينَ ﴿٨١﴾ فَمَن تَوَلَّىٰ بَعْدَ ذَٰلِكَ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْفَٰسِقُونَ ﴿٨٢﴾

**81-82.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (የመፀሐፍ ባለቤቶች ሆይ!) ነብያትን፣ መጽሐፍንና ጥበብን ሰጥቻችሁ ከዚያ ከናንተ ጋር ላለው መጽሀፍ የሚያረጋግጥ መልዕክተኛ ቢመጣላችሁ በእርሱ እንደምታምኑበት በእርግጥም እንድትረዱት ሲል ቃል ኪዳን በያዘ ጊዜ (የነበረውን ክስተት ለህዝቦችህ አስታውስ)። አረጋገጣችሁን? በዚህ ላይ ቃል ኪዳኔን ያዛችሁምን? አላቸው። እነርሱም አዎ አረጋገጥን አሉ። እንግዲያውስ መስክሩ። እኔም ከናንተ ጋር ከመስካሪዎቹ ነኝ አላቸው። እናም ከዚህ በኋላ የሸሹ ሰዎች አመፀኞቹ እነርሱ ብቻ ናቸው።

أَفَغَيْرَ دِينِ ٱللَّهِ يَبْغُونَ وَلَهُۥٓ أَسْلَمَ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ طَوْعًا وَكَرْهًا وَإِلَيْهِ
يُرْجَعُونَ ﴿٨٣﴾ قُلْ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَمَآ أُنزِلَ عَلَيْنَا وَمَآ أُنزِلَ عَلَىٰٓ إِبْرَٰهِيمَ وَإِسْمَٰعِيلَ وَإِسْحَٰقَ
وَيَعْقُوبَ وَٱلْأَسْبَاطِ وَمَآ أُوتِيَ مُوسَىٰ وَعِيسَىٰ وَٱلنَّبِيُّونَ مِن رَّبِّهِمْ لَا نُفَرِّقُ بَيْنَ أَحَدٍ
مِّنْهُمْ وَنَحْنُ لَهُۥ مُسْلِمُونَ ﴿٨٤﴾ وَمَن يَبْتَغِ غَيْرَ ٱلْإِسْلَٰمِ دِينًا فَلَن يُقْبَلَ مِنْهُ وَهُوَ فِي
ٱلْءَاخِرَةِ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٨٥﴾

**83-85.** በሰማያትና በምድር ያሉ ሁሉ በውድም ሆነ በግድ ለእርሱ የታዘዙና ወደ እርሱ የሚመለሱ ሲሆኑ (ከሐዲያን) ከአላህ ሃይማኖት ሌላን ይፈልጋሉን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ብቻ አምነናል በእኛም ላይ በተወረደው (በቁርኣን) (በነብዩ) ኢብራሂም፤ (በነብዩ) ኢስማኢል፤ (በነብዩ) ኢስሃቅም፤ (በነብዩ) የዕቆብና በነገዶች ላይ በተወረደው፤ ለነብዩ ሙሳ ለነብዩ ዒሳና ለነብያትም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጠው ሁሉ አምነናል። በእነርሱ መካከል አንድም አንለይም። እኛ ለእሱ ብቻ ታዛዦች ነን። ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ሁሉ ፈፅሞ ከእርሱ ተቀባይነት የለውም። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ* አንዱ ነው በል።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (83) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የመፅሐፍ ባለቤቶች ስለ ኢብራሂም እምነት ተከራክረው ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት ጠየቋቸው ነብዩ (ﷺ) ሁለታችሁም ከኢብራሂም እምነት ጋር ግንኙነት የላችሁም አሏቸው። በጣም ተቆጡ «የአንተን ፍርድ አንፈልግም፤ በአንተ ሀሳብም አንመራም» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዑመር ኢብኑ አል ኸጣብ እንዳስተላለፉት:- «ከእለታት አንድ ቀን ከአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጋር ተቀምጠን ሳለን አንድ በጣም ነጭ የሆነ ልብስ የለበሰ፤ ፀጉሩ በጣም የጠቆረ፤ ምንም አይነት የመንገደኛ ምልክት የማይታይበት እንዲሁም ከኛ መካከል ማንም የማያውቀው የሆነ ሰው ብቅ አለ። ጉልበቱን ከነብዩ ትክክል አሳክቶ ተቀመጠ። መዳፎቹን ደግሞ ተፋዎቹ ላይ አደረገ። «ሙሐመድ ሆይ! ስለ ኢስላም ንገረኝ» አለ። የአላህ መልዕክተኛም (ﷺ):- «ኢስላም ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው አምላክ የለም። ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፤ ሶላትን መስገድ፤ ዘካ (ምፅዋት) መስጠት፤ የረመዷን ወር መፆም፤ ከቻልክ ሐጅ ማድረግ» አሉት ጠያቂውም «እውነት ብልሃል» አለ። እሳቸውን የአላህ መልዕክተኛን (ﷺ) ጠይቆ እውነት ማለታቸውን ሲያረጋጥ በዚህ ድርጊቱ በጣም ተገረምን። ቀበል አድርጎ «ስለ እምነት ንገረኝ» አላቸው። እሳቸውም «እምነት ማለት በአላህ፤ በመላእክቶቹ (ለነብያት ባወረደው) መፅሐፎቹ በትንሳኤ ቀንና ቀድሞውኑ በተወሰኑት የአላህ ውሳኔዎች ክስተት (ቀዷ ወልቀድር) ማመን፤ ነው» አሉት። እሱም «እውነት ብልሃል» አለ። «ስለ መልካም ስነ ምግባር (አል ኢህሳን) ንገረኝ» አላቸው። እሳቸውም «መልካም ስነ ምግባር (አል ኢህሳን) ማለት አላህን እንደምትመለከተው አድረገህ መገዛት ሲሆን አንተ ባትመለከተው እሱ ግን ይመለከትሃል» አሉት። አሁን ጥያቄውን በመቀጠል «ስለ መጨረሻዋ ሰዓት ንገረኝ» አላቸው። እሳቸውም «በባርነት ውስጥ ያለች ሴት እመቤቷን ትወልዳለች፤ ጫማ የሌላቸው፤ የታረዙ፤ ድሆችና እረኞች የነበሩ ሰዎች ታላላቅ ህንፃዎችን ለመገንባት ሲፎካከሩ ታያለህ» አሉት። ከዚያ ጠያቂው ሄደ። እኔ ጥቂት ከቆየሁ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ «ጠያቂው

ማን እንደሆነ ታውቃለህን?» ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም «አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ» አልኳቸው። እሳቸውም «እርሱ በእርግጥ ጅብሪል ነው ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራችሁ ነው የመጣው» አሉኝ።

كَيْفَ يَهْدِى ٱللَّهُ قَوْمًا كَفَرُوا۟ بَعْدَ إِيمَٰنِهِمْ وَشَهِدُوٓا۟ أَنَّ ٱلرَّسُولَ حَقٌّ وَجَآءَهُمُ ٱلْبَيِّنَٰتُ ۚ
وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٨٦﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ جَزَآؤُهُمْ أَنَّ عَلَيْهِمْ لَعْنَةَ ٱللَّهِ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةِ
وَٱلنَّاسِ أَجْمَعِينَ ﴿٨٧﴾ خَٰلِدِينَ فِيهَا لَا يُخَفَّفُ عَنْهُمُ ٱلْعَذَابُ وَلَا هُمْ يُنظَرُونَ ﴿٨٨﴾
إِلَّا ٱلَّذِينَ تَابُوا۟ مِنۢ بَعْدِ ذَٰلِكَ وَأَصْلَحُوا۟ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٨٩﴾

**86-89.** ከእምነታቸውና መልዕክተኛውም እውነት መሆኑን ከመሰከሩ፤ የተብራሩ አንቀፆችም ከመጡላቸው በኋላ የካዱ ሕዝቦችን አላህ እንዴት ያቀናል፣ አላህ በዳዮችን ሕዝቦች አያቀናምና። እነዚያ መሰል ሰዎች ቅጣታቸው የአላህ የመላዕክትና የሰዎች ሁሉ እርግማን በእነርሱ ላይ መውረዱ ነው። በውስጧ ዘወታሪዎች ሲሆኑ ቅጣቱም ከእነርሱ ላይ አይቃለልላቸውም። ጊዜም አይሰጡም። እነዚያ ከዚያ በኋላም ንስሀ የገቡና ስራቸውን ያሳመሩ ሁሉ ሲቀሩ አላህ እነዚህንማ ይምራቸዋል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

የዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (86) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ የመዲና ሰው ስሙ ሀሪስ ኢብኑ ሱወይቅ ይባል የነበረ ኢስላምን ቀይሮ ወደ መካ በመሄድ እና ከዚያም በመፀፀቱ ፀፀቱን ነብዩ (ﷺ) ይቀበሉት አይቀበሉት እንደሆነ እንዲጠይቁለት ለዘመዶቹ ስለላከ ነብዩ (ﷺ) እንደሚቀበሉት ለማብሰር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። እናም ያግለሰብ ይህ አንቀፅ መውረዱ ሲነገረውና መልዕክቱ ሲነበብለት ተፀፅቶ ወደ ኢስላም መመለሱንና ጠንካራ አማኝ ሆኖ እንደነበር ተዘግቧል። (ሓኪም፤ ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ።)

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بَعْدَ إِيمَٰنِهِمْ ثُمَّ ٱزْدَادُوا۟ كُفْرًا لَّن تُقْبَلَ تَوْبَتُهُمْ وَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ
ٱلضَّآلُّونَ ﴿٩٠﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَمَاتُوا۟ وَهُمْ كُفَّارٌ فَلَن يُقْبَلَ مِنْ أَحَدِهِم مِّلْءُ ٱلْأَرْضِ
ذَهَبًا وَلَوِ ٱفْتَدَىٰ بِهِۦٓ ۗ أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ﴿٩١﴾

**90-91.** እነዚያ ከእምነታቸው በኋላ የካዱና ከዚያ ክህደትን በክህደት ላይ የጨመሩ ሰዎች ንሰሃቸው ፈፅሞ ተቀባይነት የለውም። እነዚያ የተሳሳቱ ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። እነዚያ (በአላህ አምላክነትና በነብዩ ሙሐመድ ነብይነት) የካዱና በክህደታቸው ላይ እንዳሉ የሞቱ ሰዎች፣ ከእነርሱ አንዳቸው ምድርን የሞላ ወርቅ ቤዛ ቢያቀርብም* እንኳ ፈፅሞ ተቀባይነት አያገኝም። እነዚያ ለእነርሱ የሚያሰቃይ ቅጣት አለባቸው። ለእነርሱም (ከዚህ ቅጣት) የሚያድኗቸው ምንም ረዳቶች የሏቸውም።

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በትንሳኤ ቀን በአላህ የካዳችሁ አመፀኛ ሰዎች ምድርን የሚሞላ የወርቅ ሃብት ቢኖራችሁና ከጀሀነም እሳት ለመውጣት ስትሉ ሁሉንም ልትሰጡ ትችላላችሁን? የሚል ጥያቄ ይጠየቃሉ። እነሱም እንዴታ አዎ እንሰጣለን በማለት ይመልሳሉ። ይህን ጊዜ «በምድር ላይ ሳላችሁ ከዚህ ያነሰ ጥያቄ ተጠይቃችሁ ነበር ይባላሉ።»

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (90) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁድ በነብዩ ዒሳና በኢንጅል ከመካዳቸው ባሻገር ነብዩ (ﷺ) ሲላኩ በነብዩና በቁርኣንም በመካዳቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (72-91) ያሉት አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ተንኮልና ክህደት የአይሁድ ቋሚ ባህሪ መሆኑንና አይሁድ ተንኮላቸውን፣

   ጭፍን ወገናዊነታቸውን እንዲሁም ወደ ጥፋት ለመምራት የሚጠቀሙባቸው ዘዴዎቻቸው ምን እንደሚመስሉ፣
2. አይሁድ አዕምሮአቸውን ተጠቅመው ከአላህ በተሰጣቸው ጥበብ እውነት ላይ ለመድረስ ያልቻሉ መሀይማን እንደሆኑ'
3. ይህ ማለትም ማን መከበርና ከፍ መደረግ እንዳለበት፣
4. የነብይነት ሹመትና ፀጋው ለማን እንደሚገባና ቸሮታውን የሚታደሉት እነማን እንደሆኑ የሚያውቀው አላህ ብቻ መሆኑን፣
5. አይሁድን አምኖ ከእነሱ ጋር በሚደረገው ማህበራዊ ሕይወት ጥንቃቄ መተው በእነርሱ ለመታለልና ለመሸንገል የሚዳርግ በመሆኑ በሙሉ ልብ እነርሱን ማመን አስፈላጊ ያለመሆኑን፣
6. በፈጠረው አላህ ላይ የቀጠፈ ልብና አንደበት በፍጡራን ላይ ለመዋሸት እንደማይከብደውና ይበልጥ ቀላል አድርጎ እንደሚመለከተው፣
7. አይሁድ ከእነርሱ እምነት ውጭ ያለው የሰው ዘር በሙሉ ቆሻሻ የሆነ ህዝብ እንደሆነ የሚያምኑ ከመሆኑም ባሻገር ከእነርሱ ውጪ ያለውን ሰው ንብረትና ክብር የመዳፈር የመዝረፍና የማዋረድ ሙሉ መብት እንደላቸው የሚያምኑ መሆኑን፣
8. ለገንዘብና ቁሳዊ ሀብት ብሎ ቃሉን ያፈረሰ ወይም በውሸት የማለ ሰው ወንጀሉ የከበደ መሆኑን፣

   አይሁድ ሰዎችን ለማሳሳት ተንኮላቸውን ሲሸርቡ የሚኖሩ በአላህ ላይ እና በሰዎች ላይም ለማስዋሸት ቅንጣት ያህል ሀፍረት የማይዛቸው ህዝቦች እንደሆኑ፣
9. ሙስሊም ለምድራዊ ጥቅም ብሎ እንደ አይሁዶች በውሸት መዘፈቅና ህሊናውን መሸጥ እንደማይገባው፣
10. አላህ ነብያትን ለመርዳት ካለው ፈቃደኝነት በመነሳት አንዱን ነብይ ከሌላው ነብይ ድጋፍ እንዲያገኝ ሁኔታዎችን ያመቻቸለት እንደነበር፣
11. ቃል ኪዳን በኢስላም ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ጉዳይ መሆኑን፣
12. ኢስላምን እንዲቀበሉ ጥሪ ተደርጎላቸው ያልተቀበሉ ሰዎች የተወገዙ መሆናቸውን፣
13. በከፊል ነብያትን አምኖ በከፊሉ ነብያትን መካድ ከኢስላም አጥር እንደሚያወጣ፣
14. ኢስላም ሁሉንም የአላህ ነብያትና ሁሉንም ሰማያዊ መፅሐፍትን አድሎ ሳያደርግ የሚቀበል ሀይማኖት መሆኑን፣
15. ከኢስላም ውጪ ያሉ ሃይማኖቶች ባጠቃላይ አላህ ዘንድ ተቀባይነት የሌላቸው መሆኑን፣
16. ግፍንና በወንጀል የሚያዘወትሩ ሰዎች የነበሩበትን ሙሉ በሙሉ ለመተውና ለተውበት ፈቃደኝነት እንደማይታይባቸው፣

17. በክህደት ላይ እያለ ሕይወቱ ያለፈች ሰው ከገሀነም ቅጣት ነፃ የመውጣቱ ጉዳይ ተስፋ የሌለው መሆኑን፤
18. በትንሳኤ ዕለት ነፃ ሊያወጣ የሚችለው የአላህ እዝነትና የባሪያው ስራ እንጂ ፍዳያ እንዳልሆነ እንማራለን።

لَن تَنَالُواْ ٱلۡبِرَّ حَتَّىٰ تُنفِقُواْ مِمَّا تُحِبُّونَۚ وَمَا تُنفِقُواْ مِن شَيۡءٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ بِهِۦ عَلِيمٞ ﴿٩٢﴾

**92.** *(ሙስሊሞች ሆይ!) ከምትወዱት ነገር እስከምትለግሱ ድረስ የበጎ ስራን ዋጋ (ጀነትን) አታገኙም። ከምንም ነገር ብትለግሱ አላህ ያውቀዋል።

✷ ክፍል አራት

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (92) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ቀደምት ሶሃቦች ይህን የቁርኣን አንቀፅ በተግባር ከማዋላቸው ጋር የተያያዘ በርካታ ክስተቶች በታሪክ ተላልፈውልናል። ከእነዚህም መካከል «አቡ ጦልሃ መዲና ውስጥ ከአንሷሮች ሁሉ በሀብት የላቁ ነበሩ። በመስጊዱ ፊት ለፊት «በይሩሃ» የተሰኘችን አትክልት ቦታ ከንብረቶቻቸው ሁሉ አስበልጠው ይወዳሉ። መልዕክተኛውም ይወዷታል። ከውስጧ ገብተው አረፍ ይላሉ። ከውሃዋም ይጐነጫሉ። ይህ አንቀፅ በወረደበት ወቅት አቡ ጦልሃ መልዕክተኛውን እንዲህ አሏቸው። «አላህ የምትወዱትን እስካልለገሳችሁ ድረስ መልካም ነገር አታገኙም ይላል» በይሩሀን ከንብረቶቼ ሁሉ አብልጬ እወደታለሁ ስለዚህ እርስዎ ለፈለጉት ጉዳይ ያውሉት፤ ለግሻለሁ አሉ። ኢማሙ አህመድ አነስን ዋቢ በማድረግ ተከታዩን አስተላልፈዋል።

۞ كُلُّ ٱلطَّعَامِ كَانَ حِلّٗا لِّبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ إِلَّا مَا حَرَّمَ إِسۡرَٰٓءِيلُ عَلَىٰ نَفۡسِهِۦ مِن قَبۡلِ أَن تُنَزَّلَ ٱلتَّوۡرَىٰةُۚ قُلۡ فَأۡتُواْ بِٱلتَّوۡرَىٰةِ فَٱتۡلُوهَآ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٩٣﴾ فَمَنِ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ مِنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٩٤﴾

**93-94.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተውራት ከመወረዱ በፊት ኢስራኢል በራሱ ላይ እርም ካደረገው ነገር በስተቀር ምግብ ሁሉ ለኢስራኤል ልጆች የተፈቀደ ነበር። እውነተኞች ከሆናችሁ እስኪ ተውራትን አምጡና አንብቡት በላቸው። ከዚህ በኋላ በአላህ ላይ ውሸትን የቀጣጠፉ ሰዎች እነዚያ እነርሱ ብቻ በዳዮች (በደለኞች) ናቸው።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (93) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ ኢብራሂም መንገድ ላይ ነኝ ባሉ ጊዜ «እንዴት አንተ በኢብራሂም መንገድ ላይ ትሆናለህ? የግመል ስጋ እየበላህና ወተቷን እየጠጣህ» አሏቸው። ነብዩም (ﷺ)፡- «እነዚህ እኮ ለኢብራሂም ሀላል ነበሩ» ሲሏቸው «በፍፁም እኛ ዛሬ ሃራም የምንለው ሁሉ በኑህም በኢብራሂምም ጊዜ ሃራም የነበሩ ናቸው» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

قُلۡ صَدَقَ ٱللَّهُۗ فَٱتَّبِعُواْ مِلَّةَ إِبۡرَٰهِيمَ حَنِيفٗاۖ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ﴿٩٥﴾

**95.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ እውነትን ተናገረ። (ትክክለኛ የኢብራሂም ወዳጆች ከሆናችሁ) የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲሆን ተከተሉ። ከአጋሪዎችም አልነበረም በላቸው።

إِنَّ أَوَّلَ بَيْتٍ وُضِعَ لِلنَّاسِ لَلَّذِى بِبَكَّةَ مُبَارَكًا وَهُدًى لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿٩٦﴾ فِيهِ ءَايَٰتٌۢ بَيِّنَٰتٌ
مَّقَامُ إِبْرَٰهِيمَ ۖ وَمَن دَخَلَهُۥ كَانَ ءَامِنًا ۗ وَلِلَّهِ عَلَى ٱلنَّاسِ حِجُّ ٱلْبَيْتِ مَنِ ٱسْتَطَاعَ إِلَيْهِ
سَبِيلًا ۚ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِىٌّ عَنِ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٩٧﴾

**96-97.** ለሰዎች (ማምለኪያ ይሆን ዘንድ በመሬት ላይ) ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው ቤት ብሩክና ለዓለማት ሁሉ መመሪያ ሲሆን ያ በበካህ (በመካ) ያለው ቤት (ካዕባ) ነው። በውስጡ ግልፅ የሆኑ ተዐምራቶች አሉበት። የኢብራሂምም መቆሚያ የነበረው በዉስጡ አለ። ወደ እርሱ የገባ ሰው ሁሉ ሰላም ይሆናል። ለአላህ ከሰዎች መካከል ወደ እርሱ የመሄድን ጣጣ በቻለ ሰው ሁሉ ላይ ቤቱን መጎብኘት ግዴታ አለበት። በአላህ የካደ ሰው ግን እራሱን እንጂ ማንንም አይጎዳም። አላህ ከዓለማት ሁሉ የተብቃቃ ነውና።

قُلْ يَٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ لِمَ تَكْفُرُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَٱللَّهُ شَهِيدٌ عَلَىٰ مَا تَعْمَلُونَ ﴿٩٨﴾ قُلْ يَٰٓأَهْلَ
ٱلْكِتَٰبِ لِمَ تَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ مَنْ ءَامَنَ تَبْغُونَهَا عِوَجًا وَأَنتُمْ شُهَدَآءُ ۗ وَمَا ٱللَّهُ
بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعْمَلُونَ ﴿٩٩﴾

**98-99.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ! አላህ በምትሰሩት ሁሉ ላይ አዋቂ ሲሆን በአላህ ተዐምራቶቹ ለምን ትክዳላችሁ?። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ! እናንተ መስካሪዎች ሆናችሁ ከአላህ መንገድ መጥመምን የምትፈልጉት ስትሆኑ ያመነን ሰው ለምን ትከለክላላችሁ? አላህ ከምትሰሩት ነገር ላይ ሁሉ ዘንጊ አይደለም በላቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِن تُطِيعُوا۟ فَرِيقًا مِّنَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ يَرُدُّوكُم بَعْدَ إِيمَٰنِكُمْ
كَٰفِرِينَ ﴿١٠٠﴾ وَكَيْفَ تَكْفُرُونَ وَأَنتُمْ تُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ ءَايَٰتُ ٱللَّهِ وَفِيكُمْ رَسُولُهُۥ ۗ وَمَن
يَعْتَصِم بِٱللَّهِ فَقَدْ هُدِىَ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿١٠١﴾

**100-101.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በእነዚያ መጽሐፉን ከተሰጡት ሰዎች መካከል ከፊሎቹን ባሏችሁ ነገር ሁሉ ብትታዘዙ ከእምነታችሁ በኋላ ወደ ክህደት ይመልሷችኋል። የአላህ አንቀፆች በእናንተ ላይ እየተነበቡና መልዕክተኛውም በውስጣችሁ እያለ እንዴት በአላህ ትክዳላችሁ? በአላህ የሚጠበቅ ሰው ሁሉ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ሁሉ በእርግጥ ተመራ።

*ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከ (100-101) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- በጃሂሊያ ዘመን ዐውስና በኸዝረጅ የተባሉ ሁለት ብሔሮች መካከል ለብዙ ዘመናት የቆየ ጦርነትና ጭቅጭቅ ነበር። ኢስላም በመጣበት ወቅት ግን አንድነት ፈጥረው ብዙ ቁም ነገሮችን ከሰሩ በኋላ ከእለታት አንድ ቀን የሁለቱም ወገኖች ባሉበት ቦታ አንድ አይሁድ በቀድሞው ዘመን ከሁለቱ ብሔሮች የአንደኛው ብሄር አባል የሆነ ገጣሚ የቋጠረውን ግጥም አስታወሳቸው። በዚህም ስሜታቸው ተነሳስቶ የድሮ ቁርሾአቸውን ለመመለስ ሲፎካከሩና ለጦርነት ሲዘጋጁ ይህ አንቀፅ ወረደ። ነብዩም (ﷺ) በመሀከላቸው ሆነው አነበቧት። እነሱም በሰሟት ጊዜ ሁሉም ጦሩን በመጣል አንገት ለአንገት ተቃቅፈው እየተላቀሱ ተሳሳሙ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)*

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ تُقَاتِهِۦ وَلَا تَمُوتُنَّ إِلَّا وَأَنتُم مُّسْلِمُونَ ﴿١٠٢﴾ وَٱعْتَصِمُوا۟ بِحَبْلِ ٱللَّهِ جَمِيعًا وَلَا تَفَرَّقُوا۟ ۚ وَٱذْكُرُوا۟ نِعْمَتَ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ كُنتُمْ أَعْدَآءً فَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِكُمْ فَأَصْبَحْتُم بِنِعْمَتِهِۦٓ إِخْوَٰنًا وَكُنتُمْ عَلَىٰ شَفَا حُفْرَةٍ مِّنَ ٱلنَّارِ فَأَنقَذَكُم مِّنْهَا ۗ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمْ ءَايَـٰتِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ ﴿١٠٣﴾ وَلْتَكُن مِّنكُمْ أُمَّةٌ يَدْعُونَ إِلَى ٱلْخَيْرِ وَيَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ ۚ وَأُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿١٠٤﴾ وَلَا تَكُونُوا۟ كَٱلَّذِينَ تَفَرَّقُوا۟ وَٱخْتَلَفُوا۟ مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَهُمُ ٱلْبَيِّنَـٰتُ ۚ وَأُو۟لَـٰٓئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ عَظِيمٌ ﴿١٠٥﴾

**102-105.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን የሚገባውን ያህል ተጠንቀቁት ፍሩት። እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) የአላህን ጠንካራ የእምነት ገመድም ሁላችሁም በአንድ ሁናችሁ ያዙ። አትለያዩ፡ ጠበኞች በነበራችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ የዋለውን የአላህን ፀጋም አስታውሱ። በልቦቻችሁም መካከል አስማማ በፀጋውም ወንድማማቾች ሆናችሁ። በእሳት ጉድጓድ አፋፍ ላይ ነበራችሁና ከእርሷም አዳናችሁ። ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትመሩ ዘንድ አላህ ለእናንተ አናቅፅን ልክ እንደዚሁ ያብራራል። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ከናንተ መካከል ወደ በጎ ነገር የሚጠሩና በመልካም ስራ የሚያዙ ከከፋ ነገር የሚከለክሉ ከፊሎች ቡድኖች ይኑሩ። እነዚያ ከእሳት የሚድኑ እነርሱ

ናቸው። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እንደነዚያ ግልፅ ተዐምራት ከመጣላቸው በኋላ እንደተለያዩትና እንደተጨቃጨቁት (የመፅሐፍ ሰዎች) አትሁኑ። እነዚያም ለነርሱ ታላቅ ቅጣት አለባቸው።

يَوْمَ تَبْيَضُّ وُجُوهٌ وَتَسْوَدُّ وُجُوهٌ ۚ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ٱسْوَدَّتْ وُجُوهُهُمْ أَكَفَرْتُم بَعْدَ إِيمَٰنِكُمْ فَذُوقُوا۟ ٱلْعَذَابَ بِمَا كُنتُمْ تَكْفُرُونَ ﴿١٠٦﴾ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ ٱبْيَضَّتْ وُجُوهُهُمْ فَفِى رَحْمَةِ ٱللَّهِ ۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿١٠٧﴾

**106-107.** (የአማኞች) ፊቶች የሚያበሩበትና (የከሐዲያን) ፊቶችም የሚጠቁሩበትን ቀን (አስታውስ)። እነዚያ ፊቶቻቸው የጠቆሩት ወገኖች ከእምነታችሁ በኋላ ካዳችሁን? ትክዱ የነበራችሁትን ነገር ቅጣቱን ቅመሱ (ይባላሉ)። እነዚያ ፊቶቻቸው ያበሩት ወገኖች ደግሞ በአላህ ችሮታ ገነት ውስጥ ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘወታሪዎች ናቸው።

تِلْكَ ءَايَٰتُ ٱللَّهِ نَتْلُوهَا عَلَيْكَ بِٱلْحَقِّ ۗ وَمَا ٱللَّهُ يُرِيدُ ظُلْمًا لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿١٠٨﴾ وَلِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ وَإِلَى ٱللَّهِ تُرْجَعُ ٱلْأُمُورُ ﴿١٠٩﴾

**108-109.** እነኚህ በአንተ ላይ በእውነት የምናነባቸው የአላህ አንቀፆች ናቸው። አላህ ለዓለማት በደልን የሚሻ አይደለም።* በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለ ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። ነገሮች ሁሉ የኋላ ኋላ ወደ አላህ ብቻ ይመለሳሉ።

كُنتُمْ خَيْرَ أُمَّةٍ أُخْرِجَتْ لِلنَّاسِ تَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ وَتَنْهَوْنَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ وَتُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ ۗ وَلَوْ ءَامَنَ أَهْلُ ٱلْكِتَٰبِ لَكَانَ خَيْرًا لَّهُم ۚ مِّنْهُمُ ٱلْمُؤْمِنُونَ وَأَكْثَرُهُمُ ٱلْفَٰسِقُونَ ﴿١١٠﴾

**110.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ለሰው ልጆች ጥቅም (አገልግሎት) ከተገለፁት ሕዝቦች ሁሉ በላጭ ሆናችሁ። ይኸውም በመልካም ነገር ታዛላችሁ። ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ። በአላህም አንድነት ታምናላችሁና ነው።* የመጽሐፍ ሰዎችም ልክ እንደናንተ ባመኑ ኑሮ ለእነርሱ የተሻለ በሆነ ነበር። ጥቂትም ቢሆኑ ትክክለኛ ከእነርሱ መካከል አማኞች አሉ። አብዛሀኞቻቸው ግን አመፀኞች ናቸው።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (110) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ አይሁዶች ለአንዳንድ ሙስሊሞች «እኛ እኮ ከእናንተ እንሻላለን። እምነታችንም ከእናንተ እምነት ይበልጣል» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

✶ አቡ ሁረይራህ እንዲህ ብለዋል፡- «ለሰዎች ከተገለፀች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ» ማለት ለሰዎች መልካም የሆኑ ሰዎች ማለት ነው። ሰዎች በአንገታቸው ላይ ሰንሰለት እንደተጠለቀ ኢስላምን እስከሚቀበሉ ድረስ የምታመጧቸው ናችሁ» አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በሰንሰለት ታስረው ወደ ጀነት በሚገቡ ሰዎች አላህ ይደነቃል»

እዚህ ላይ በሰንሰለት የታሰሩ ሰዎች የሚያመለክተው ምናልባት በጦርነት ተማርከው የተያዙ የጦር ምርኮኞችን ሲሆን ይህ ሰንሰለት መታሰራቸውን ኢስላምን ለመቀበል ሁነኛ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላል። ስለዚህ ሰንሰለታቸው ጀነትን የመቀዳጃ ምክንያታቸው ነው።

لَن يَضُرُّوكُمْ إِلَّآ أَذًى ۖ وَإِن يُقَـٰتِلُوكُمْ يُوَلُّوكُمُ ٱلْأَدْبَارَ ثُمَّ لَا يُنصَرُونَ ﴿١١١﴾ ضُرِبَتْ عَلَيْهِمُ
ٱلذِّلَّةُ أَيْنَ مَا ثُقِفُوٓا۟ إِلَّا بِحَبْلٍ مِّنَ ٱللَّهِ وَحَبْلٍ مِّنَ ٱلنَّاسِ وَبَآءُو بِغَضَبٍ مِّنَ ٱللَّهِ وَضُرِبَتْ
عَلَيْهِمُ ٱلْمَسْكَنَةُ ۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ كَانُوا۟ يَكْفُرُونَ بِـَٔايَـٰتِ ٱللَّهِ وَيَقْتُلُونَ ٱلْأَنۢبِيَآءَ بِغَيْرِ حَقٍّ ۚ
ذَٰلِكَ بِمَا عَصَوا۟ وَّكَانُوا۟ يَعْتَدُونَ ﴿١١٢﴾

**111-112.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ከሓዲያን ማስከፋት ያህልን እንጅ ፈፅሞ አይጎዷችሁም። ቢዋጓችሁም ጀርባዎችን ያዞሩላችኋል (ይሸሻሉ) ከዚያ በምንም ረዳት አያገኙም። በየተገኙበት ስፍራ ከአላህም ሆነ ከሰዎች በሆነ ቃል ኪዳን የተጠበቁ ካልሆኑ በስተቀር በእነርሱ ላይ ውርደት ተመቶባቸዋል። (ተፅፎባቸዋል)። ይህ የሆነው በአላህ ተዐምራት (አንቀፅ) ይክዱ ስለነበሩ ነው። ይህም የሆነው በማመጻቸውና ወሰንን ይተላለፉ ስለነበሩ ነው።

۞ لَيْسُوا۟ سَوَآءً ۗ مِّنْ أَهْلِ ٱلْكِتَـٰبِ أُمَّةٌ قَآئِمَةٌ يَتْلُونَ ءَايَـٰتِ ٱللَّهِ ءَانَآءَ ٱلَّيْلِ وَهُمْ
يَسْجُدُونَ ﴿١١٣﴾ يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ وَيَأْمُرُونَ بِٱلْمَعْرُوفِ وَيَنْهَوْنَ عَنِ ٱلْمُنكَرِ
وَيُسَـٰرِعُونَ فِى ٱلْخَيْرَٰتِ ۖ وَأُو۟لَـٰٓئِكَ مِنَ ٱلصَّـٰلِحِينَ ﴿١١٤﴾ وَمَا يَفْعَلُوا۟ مِنْ خَيْرٍ فَلَن يُكْفَرُوهُ ۗ
وَٱللَّهُ عَلِيمٌۢ بِٱلْمُتَّقِينَ ﴿١١٥﴾

**113-115.** የመጽሐፍ ባለቤቶች ሁሉ በእምነት እኩል አይደሉም። ከመፅሐፍ ባለቤቶች መካከል ቀጥ ያሉና በሌሊት ሰዓቶች እየሰገዱ የአላህን አንቀፆች የሚያነቡ ሕዝቦች አሉና። በአላህና በመጨረሻውም ቀን ያምናሉ። በፅድቅም ነገር ያዛሉ። ከመጥፎ ነገርም ይከለክላሉ። ለበጎ ስራዎችም ይጣደፋሉ። እነርሱ ከደጋግ ሰዎች ናቸው። ከበጎ ስራ ሰሪዎች መካከል ማንኛውንም በጎ ስራ ቢሰሩ አይካዱትም ውድቅ አይደረግባቸውም። አላህ ጥንቁቆቹን ሁሉ አዋቂ ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከ (111-113) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የአይሁድ መሪዎች ኢስላምን በተቀበሉ ጓደኞቻቸው በተለየ መልክ ጉዳት ለማድረስ ይንቀሳቀሱ ስለነበር እነሱን ለማፅናናት የወረዱ አናቅፅ ናቸው። (ዋሒዲ)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፉ ከአንቀፅ (92-115) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መልካም ስራ እንደመልካም ታይቶ ምንዳ የሚያስገኘው በሙሉ ልብና ወዴታ ሲሰራ መሆኑን፤
2. አይሁድ አዋቂዎችን መከተል ወደ ተሳሳተው መንገድ የሚከት አደጋ መሆኑን፤
3. መዳን የሚቻለው ቁርኣንና ሐዲስ በማወቅና የእነሱን ትዕዛዛትና መመሪያዎች በመከተል ብቻ መሆኑን፤
4. ኢስላምን እጥብቆ መያዝ በዱንያም ሆነ በአኼራ ሊያጋጥም ከሚችል ኪሳራ ነፃ እንደሚደርግ፤
5. በሽርክና በወንጀል ላይ መዘወተር ወደ ገሀነም ለመውረድ አፋፍ ላይ ሆኖ እንደመክረም እንደሚቆጠር፤
6. ከሙስሊሞች መካከል የተወሰኑ ሰዎች ሃይማኖቱን ለማስተማር ሙሉ ጊዜያቸውን የሰጡ መሆን እንዳለባቸው፤
7. በሙስሊሞች መሀከል ልዩነት የሚፈጥሩና ክፍተት የሚያሳልፉ ክርክሮችና ጭቅጭቆች የተከለከሉ መሆናቸውን፤
8. በኢስላም መሰረት ፈጠራዎችን (ቢድዐዎች) የሚያራምዱ ሰዎች በቂያማ (በትንሳኤ) ዕለት ፊታቸው ከሰል መስሎ እንደሚታይና በዚሁ ምልክታቸው የተነሳ ተለይተው እንደሚታወቁ።
9. ነብዩ (ﷺ) የሕይወትና የዲን ስርዓት ነጥብ በነጥብ የሚከተሉ የሃይማኖቱን ስርዓት ሳይጨምሩ ሳይቀንሱ የሚተገብሩ ሰዎች ማለትም የነብዩ (ﷺ) ፈለግ የሚከተሉ የሱና ሰዎች ደግሞ ፊታቸው ላይ ብርሃን ፈንጥቆና ፊታቸው ቀይ ሆኖ እንደሚታይ፤
10. አላህ ለነብዩ (ﷺ) የተለየ ክብርና ማዕረግ እንደሰጣቸው፤
11. ለዱንያም ሆነ ለአኼራ ጉዳዩች ብቸኛው ባለቤትና መፍትሄ ሰጪ አላህ በመሆኑ ለሁሉም ጉዳይ ፊትን ወደ እርሱ ማዞር ተገቢ መሆኑን
12. እውነትን ይዞ በዒባዳ ላይ መፅናት ያለውን መጠነ ሰፊ ምንዳ፤
13. ውድቅት ሌሊት ላይ ቁርኣንን በተመስጦ ማንበብ ሶላትን መስገድ ወንጀልን እንደሚያሰርዝ፤ ፀሎትን ተቀባይ የሚያደርግ፤ ጥሩ ደረጃን የሚያስገኝ የዒባዳ አይነት መሆኑን፤
14. በመልካም ተግባራት ላይ ውድድርና እሽቅድድም ማድረግ እጅግ ተወዳጅ እንደሆነ፤
15. የመፅሐፍ ሰዎች ከሆኑት አይሁድና ነሳራዎች መሀከል የኢስላምን ጥሪ (ዳዕዋ) በማድመጥ ወደ ኢስላም ትክክለኛ እምነት የገቡ ሰዎች የሚያገኙት ምንዳ (አጅር) ከፍተኛ መሆኑን እንማራለን።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَن تُغْنِىَ عَنْهُمْ أَمْوَٰلُهُمْ وَلَآ أَوْلَٰدُهُم مِّنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔا ۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ
ٱلنَّارِ ۚ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿١١٦﴾ مَثَلُ مَا يُنفِقُونَ فِى هَٰذِهِ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا كَمَثَلِ رِيحٍ فِيهَا صِرٌّ
أَصَابَتْ حَرْثَ قَوْمٍ ظَلَمُوٓاْ أَنفُسَهُمْ فَأَهْلَكَتْهُ ۚ وَمَا ظَلَمَهُمُ ٱللَّهُ وَلَٰكِنْ أَنفُسَهُمْ يَظْلِمُونَ ﴿١١٧﴾

**116-117.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ገንዘቦቻቸውና ልጆቻቸው ከአላህ (ቅጣት) ምንንም አያድኗቸውም። እነዚያም የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በእርሷ ውስጥም ዘውታሪዎች ናቸው። የዚያ በዚህች በቅርቢቱ ሕይወት የሚለግሱትን ነገር ሁሉ ምሳሌው በውስጧ ውርጭ ያለባት ነፋስ ነፍሶቻቸውን የበደሉን ሕዝቦች አዝመራ እንደነካችና እንዳጠፋችው ብጤ ነው። በዚህም አላህ አልበደላቸውም ግን እነርሱ ነፍሶቻቸውን በእራሳቸው ይበድላሉ እንጂ።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَتَّخِذُوا۟ بِطَانَةً مِّن دُونِكُمْ لَا يَأْلُونَكُمْ خَبَالًا وَدُّوا۟ مَا عَنِتُّمْ قَدْ
بَدَتِ ٱلْبَغْضَآءُ مِنْ أَفْوَٰهِهِمْ وَمَا تُخْفِى صُدُورُهُمْ أَكْبَرُ ۚ قَدْ بَيَّنَّا لَكُمُ ٱلْـَٔايَـٰتِ ۖ إِن كُنتُمْ
تَعْقِلُونَ ﴿١١٨﴾ هَـٰٓأَنتُمْ أُو۟لَآءِ تُحِبُّونَهُمْ وَلَا يُحِبُّونَكُمْ وَتُؤْمِنُونَ بِٱلْكِتَـٰبِ كُلِّهِۦ وَإِذَا لَقُوكُمْ
قَالُوٓا۟ ءَامَنَّا وَإِذَا خَلَوْا۟ عَضُّوا۟ عَلَيْكُمُ ٱلْأَنَامِلَ مِنَ ٱلْغَيْظِ ۚ قُلْ مُوتُوا۟ بِغَيْظِكُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ
عَلِيمٌۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿١١٩﴾ إِن تَمْسَسْكُمْ حَسَنَةٌ تَسُؤْهُمْ وَإِن تُصِبْكُمْ سَيِّئَةٌ يَفْرَحُوا۟ بِهَا ۖ
وَإِن تَصْبِرُوا۟ وَتَتَّقُوا۟ لَا يَضُرُّكُمْ كَيْدُهُمْ شَيْـًٔا ۗ إِنَّ ٱللَّهَ بِمَا يَعْمَلُونَ مُحِيطٌ ﴿١٢٠﴾

**118-120.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከናንተ ሌላ የሆኑን አካሎች ሚስጥረኛ አድርጋችሁ (የልብ ወዳጅን) አትያዙ። የእናንተን ጉዳይ ከማበላሸት አይቦዝኑላችሁምና። ሁልጊዜም ጉዳታችሁን ይወዳሉና (ይመኛሉ) ለእናንተ ያላቸው ጥላቻ ከአፎቻቸው ላይ እንኳ ተገለፀ። በልቦቻቸው የሚደብቁት ደግሞ ከዚህ ይበልጥ የከፋ ነው። ልብ የምታደርጉ እንደሆናችሁ ለእናንተ ማብራሪያዎችን በእርግጥ ገለፅን። እናንተ ትወዷቸዋላችሁ። እነርሱ ግን በፍፁም አይወዷችሁም። እናንተ በሁሉም መጽሐፍ ታምናላችሁ። እነርሱ ግን ባገኙዋችሁ ጊዜ አምነናል ይላሉ። ከናንተ ባገለሉ ጊዜ ግን ከቁጭታቸው የተነሳ በእናንተ ላይ ዐጥቆቻቸውን (ጣቶቻቸውን) ይነክሳሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተቆጭታችሁ ሙቱ። አላህ ልቦችን የቋጠሩትን ሁሉ አዋቂ ነውና በላቸው። በህይወታችሁ ደግ ነገር ብታገኙ ይከፋቸዋል። መጥፎ ነገር ቢደርስባችሁ ግን ይደሰታሉ። ከታገሳችሁና አላህን ከፈራችሁ ተንኮላቸው ምንም አይጎዳችሁም። አላህ ለሚሰሩት ሁሉ (በዕውቀቱ) ከባቢ ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (118) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከሙዕሚኖች መካከል አንዳንዶቹ በስጋ ከሚገናኙ አንዳንድ አስመሳዮችና አይሁዶች ጋር የነበራቸውን ግንኙነት በተመለከተ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَإِذْ غَدَوْتَ مِنْ أَهْلِكَ تُبَوِّئُ ٱلْمُؤْمِنِينَ مَقَٰعِدَ لِلْقِتَالِۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿١٢١﴾
إِذْ هَمَّت طَّآئِفَتَانِ مِنكُمْ أَن تَفْشَلَا وَٱللَّهُ وَلِيُّهُمَاۗ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ﴿١٢٢﴾

**121-122.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምዕመናንን ለውጊያ ስፍራዎች የምታዘጋጅ ሆነህ ከቤተሰብህ በጧት በወጣህ ጊዜ የሆነውን (አስታውስ)። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነውና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ረዳታችሁ ሲሆን በእናንተ መካከል ሁለት ቡድኖች (ወገኖች) ለመፍራት ባሰቡ ጊዜ የሆነውን (አስታውስ)። በአላህ ላይ ብቻ አማኞች ሁሉ ይመኩ።

وَلَقَدْ نَصَرَكُمُ ٱللَّهُ بِبَدْرٍ وَأَنتُمْ أَذِلَّةٌۖ فَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴿١٢٣﴾
إِذْ تَقُولُ لِلْمُؤْمِنِينَ أَلَن يَكْفِيَكُمْ أَن يُمِدَّكُمْ رَبُّكُم بِثَلَٰثَةِ ءَالَٰفٍ مِّنَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ
مُنزَلِينَ ﴿١٢٤﴾ بَلَىٰٓۚ إِن تَصْبِرُوا۟ وَتَتَّقُوا۟ وَيَأْتُوكُم مِّن فَوْرِهِمْ هَٰذَا يُمْدِدْكُمْ رَبُّكُم بِخَمْسَةِ
ءَالَٰفٍ مِّنَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ مُسَوِّمِينَ ﴿١٢٥﴾ وَمَا جَعَلَهُ ٱللَّهُ إِلَّا بُشْرَىٰ لَكُمْ وَلِتَطْمَئِنَّ قُلُوبُكُم
بِهِۦۗ وَمَا ٱلنَّصْرُ إِلَّا مِنْ عِندِ ٱللَّهِ ٱلْعَزِيزِ ٱلْحَكِيمِ ﴿١٢٦﴾ لِيَقْطَعَ طَرَفًا مِّنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟
أَوْ يَكْبِتَهُمْ فَيَنقَلِبُوا۟ خَآئِبِينَ ﴿١٢٧﴾

**123-127.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በበድር ዘመቻ ዕለት እናንተ ጥቂቶች ሆናችሁ ሳለ በእርግጥ ረዳችሁ። አላህን ታመሰግኑ ዘንድ ፍሩት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለምዕመናን ጌታችሁ ሶስት ሽህ መላዕክትን የተወረዱ ሲሆኑ ቢረዳችሁ አይበቃችሁምን? በምትል ጊዜ የሆነውን አስታውስ። አዎን (እንዴት) ብትታገሱና ብትጠነቀቁ አሁኑኑ በፍጥነት ጠላቶቻችሁ ቢመጡባችሁ ጌታችሁ ምልክት ባላቸው አምስት ሺህ መላዕክት ይረዳችኋል። አላህ ለእናንተ ብስራትና ልቦቻችሁ በእርሱ እንዲረኩ እንጂ እርዳታውን ለምንም አላደረገውም። ድልም አሸናፊና ጥበበኛ ከሆነው ከአላህ ዘንድ ብቻ እንጂ ከሌላ ከማንም የሚገኝ አይደለም።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከ (121-127) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- በኡሁድ ዘመቻ ጉዳይና አፈፃፀም እንዴት እንደነበር የሚገልፁ አናቅፅ ናቸው። (ዋሒዲ)

لَيۡسَ لَكَ مِنَ ٱلۡأَمۡرِ شَيۡءٌ أَوۡ يَتُوبَ عَلَيۡهِمۡ أَوۡ يُعَذِّبَهُمۡ فَإِنَّهُمۡ ظَٰلِمُونَ ١٢٨ وَلِلَّهِ مَا فِي
ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۚ يَغۡفِرُ لِمَن يَشَآءُ وَيُعَذِّبُ مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ١٢٩

**128-129.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱ ራሳቸውን በዳዩች ናቸውና አላህ በእነርሱ ላይ ከፈለገም ይቅርታ እስከሚያደርግ ወይም በጥፋታቸው እስኪቀጣቸው ድረስ ለአንተ በነገሩ እነርሱ ጉዳይ ላይ ምንም የለህም። በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ ስልጣን የአላህ ብቻ ነው። ለፈለገው ሰው ይምራል። የሚፈለገውን ሰው ይቀጣል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (128) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በኡሁዱ ዘመቻ ቀን ጥርሳቸው ተሰብሮ፤ ግንባራቸው ተፈንክቶ፤ በፊታቸው ላይ ደም እየፈሰሰ ወደ አላህ የሚጠራቸውን ነብይ ፊት በደም የለቀለቁ ሰዎች እንዴት ነፃ ይወጣሉ በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَأۡكُلُواْ ٱلرِّبَوٰٓاْ أَضۡعَٰفٗا مُّضَٰعَفَةٗۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ١٣٠
وَٱتَّقُواْ ٱلنَّارَ ٱلَّتِيٓ أُعِدَّتۡ لِلۡكَٰفِرِينَ ١٣١ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ١٣٢
۞وَسَارِعُوٓاْ إِلَىٰ مَغۡفِرَةٖ مِّن رَّبِّكُمۡ وَجَنَّةٍ عَرۡضُهَا ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ أُعِدَّتۡ لِلۡمُتَّقِينَ ١٣٣

**130-133.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አራጣን* የተነባበሩ እጥፎች ሲሆኑ አትብሉ። ከገሀነም እሳት ትድኑም ዘንድ አራጣን በመተው አላህን ፍሩ። ያችን ለከሓዲያን የተደገሰችውን የገሀነም እሳት ተጠንቀቁ። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ። ወደ ጌታችሁ ምህረትና ስፋቷ እንደ ሰባቱ ሰማያትና ምድር ያክል ወደ ሆነችው ገነት አላህን ለሚፈሩ የተዘጋጀች ስትሆን ተቻኮሉ።

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከሰባት ከባባድ ወንጀሎች ራቁ» ሰዎችም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነማን ናቸው?» ሲሉ ጠየቁ። እሳቸውም «በአላህ ላይ ማጋራት፤ ድግምት፤ ትክክለኛ በሆነ መንገድ ካልሆነ በስተቀር አላህ ክልክል ያደረጋትን ነፍስ መግደል፤ ወለድ መብላት፤ የሙት ህፃናትን ገንዘብ መብላት፤ በጦርነት ውስጥ ጀርባን ሰጥቶ መሸሽ፤ ጥብቅ የሆኑ ሙእሚን ሴቶችን በዝሙት ወንጀል ስማቸውን ማጥፋት»

ٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ فِي ٱلسَّرَّآءِ وَٱلضَّرَّآءِ وَٱلۡكَٰظِمِينَ ٱلۡغَيۡظَ وَٱلۡعَافِينَ عَنِ ٱلنَّاسِۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ
ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٣٤ وَٱلَّذِينَ إِذَا فَعَلُواْ فَٰحِشَةً أَوۡ ظَلَمُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ ذَكَرُواْ ٱللَّهَ فَٱسۡتَغۡفَرُواْ لِذُنُوبِهِمۡ
وَمَن يَغۡفِرُ ٱلذُّنُوبَ إِلَّا ٱللَّهُ وَلَمۡ يُصِرُّواْ عَلَىٰ مَا فَعَلُواْ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ١٣٥ أُوْلَٰٓئِكَ جَزَآؤُهُم
مَّغۡفِرَةٞ مِّن رَّبِّهِمۡ وَجَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ وَنِعۡمَ أَجۡرُ ٱلۡعَٰمِلِينَ ١٣٦

**134-136.** ለእነዚያ በድሎትም ሆነ በችግር*1 ጊዜ ለሚለግሱት ቁጭትንም ገቺዎች*2 ለሰዎችም ይቅርታ አድራጊዎች ለሆኑት፤ አላህ በጎ ሰሪዎችን ሁሉ ይወዳልና። ለእነዚያ መጥፎ ስራን በሰሩ ወይም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ አላህን የሚያስታውሱና ለኃጢአቶቻቸው ምህረትን የሚለምኑ ለሆኑት ተደግሳለች። ከአላህ ሌላ ኃጢአቶችን የሚምር አንድም የለም። በስህተት በሰሩት ላይ እነርሱ የሚያውቁ ሲሆኑ የማይዘወትሩ ለሆኑት ተደግሳለች። እነዚያ ምንዳቸው ከጌታቸው ምህረትና በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ በስሮቻቸቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶችም ናቸው። የመልካም ሰሪዎች ሁሉ ምንዳ የሆነችው ገነት ምንኛ አማረች!።

*1 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «እያንዳንዱ የሰው ልጅ መገጣጠሚያ ልክ ሰደቃህ ግዴታ አለበት። አንድን ሰው መጓጓዣ ላይ እንዲወጣ ብትረዳው፤ ወይም ጓዙን ብታቀብለው ይህች አድራጎት ሰደቃ ናት። መልካም ንግግር ሰደቃ ናት። ወደ መስጂድ የምታደርገው እያንደንዷ እርምጃ ሰደቃ ናት። ለአንድ ሰው መንገድ ማመላከት ሰደቃ ነው» (ቡኻሪ)

*2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «ከሰዎች መካከል ብርቱ ማለት ሰዎችን በጥንካሬው የሚበልጥ አይደለም። ነገር ግን ብርቱ ሰው ማለት በንዴት ወቅት ራሱን የሚቆጣጠር ነው።»

የዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (135) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- አንድ ነብሃን የተባለ ተምር ሻጭ አንዲት ቆንጆ ሴት መጥታ ተምር ስትገዛው አቅፎ ከሳማት በኋላ በዚህ ተግባሩ ተፀፅቶ ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት ድርጊቱን በመናገሩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِكُمْ سُنَنٌ فَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَٱنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلْمُكَذِّبِينَ ﴿١٣٧﴾
هَٰذَا بَيَانٌ لِّلنَّاسِ وَهُدًى وَمَوْعِظَةٌ لِّلْمُتَّقِينَ ﴿١٣٨﴾

**137-138.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ከናንተ በፊት ብዙ ድርጊቶች በእርግጥ አልፈዋል። በምድር ላይ ሂዱና ያስተባባዮች ፍፃሜው እንዴት እንደነበረ ተመልከቱ። ይህ ቁርኣን ለሰዎች ሁሉ ገላጭ ለጥንቁቆች ብቻ መሪና ገሳጭ ነው።

وَلَا تَهِنُوا۟ وَلَا تَحْزَنُوا۟ وَأَنتُمُ ٱلْأَعْلَوْنَ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿١٣٩﴾ إِن يَمْسَسْكُمْ قَرْحٌ فَقَدْ
مَسَّ ٱلْقَوْمَ قَرْحٌ مِّثْلُهُۥ ۚ وَتِلْكَ ٱلْأَيَّامُ نُدَاوِلُهَا بَيْنَ ٱلنَّاسِ وَلِيَعْلَمَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟
وَيَتَّخِذَ مِنكُمْ شُهَدَآءَ ۗ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٤٠﴾ وَلِيُمَحِّصَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَيَمْحَقَ
ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿١٤١﴾ أَمْ حَسِبْتُمْ أَن تَدْخُلُوا۟ ٱلْجَنَّةَ وَلَمَّا يَعْلَمِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ جَٰهَدُوا۟ مِنكُمْ وَيَعْلَمَ
ٱلصَّٰبِرِينَ ﴿١٤٢﴾ وَلَقَدْ كُنتُمْ تَمَنَّوْنَ ٱلْمَوْتَ مِن قَبْلِ أَن تَلْقَوْهُ فَقَدْ رَأَيْتُمُوهُ وَأَنتُمْ تَنظُرُونَ ﴿١٤٣﴾

**139-143.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እናንተ የበላዮች ናችሁና ትክክለኛ ምዕመናን እንደሆናችሁ (አትስነፉ)። አትድከሙ። አትዘኑም። (አማኞች ሆይ!) የመቁሰል ጉዳት ቢያገኛችሁ ሌሎች ህዝቦችም መሰሉ የመቁሰል ጉዳት አግኝቷቸዋል። እንዲህ አይነቶችን ቀናት በሰዎች መካከል እናፈራርቃቸዋለን። አላህ እነዚያን በትክክል በሱ ያመኑትን ሊያውቅና (እንዲለይ) ከእናተም መካከል ሰማዕታትን ሊመርጥ እንዲህ አይነት ቀናት እንዲፈራረቁ ያደርጋል። አላህ በዳዩችን ሁሉ አይወድምና። አላህ እነዚያን በትክክል በሱ ያመኑትን ከኃጢአት ሊያነፃና ከሐዲያንንም ሊያጠፋ ነው ይህን ያደረገው። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) አላህ ከናንተ መካከል እነዚያን የታገሉትንና ታጋሾችን ሳያሳውቅ (ሳይለይ) ገነትን የምትገቡ መሰላችሁን? በጦርነት ላይ መሞትን ሳታገኙት በፊት የምትመኙት ነበራችሁ። እናንተም በአይናችሁ የምትመለከቱ ስትሆኑ በእርግጥ አያችሁት። (ታዲያ ለምን ከእሱ ሸሻችሁ?)

ከዒምራን ቤተሰቦች ምእራፍ **(139)** ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የኡሁድ ጦርነት ቀን ሙስሊሞች ተሸንፈው ባሉበት ኻሊድ ኢብኑወሊድ የከሓዲያንን ፈረሶች በመምራት በጋራው በኩል ሲመጣ ነብዩ (ﷺ) «ጌታዬ ሆይ ያለ አንተ ለእኛ ሀይል የለንም በዚች ሀገር ከእነዚህ ቡድኖች ሌላ የሚገዛህ የለም» በማለታቸው እና ሙስሊሞች በሞራል ተነሳስተው በመካከላቸው ማሸነፋቸውን ለመግለፅ የወረደ አንቀፅ ነው። (ዋሒዲ)

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ **(140)** ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በኡሁድ ጦርነት ቀን ባጋጠማቸው ሽንፈት አዝነው ሴቶች የባሎቻቸውን እና የልጆቻቸውን ሞት እየተረዱ ባሉበት ሰዓት ነብዩ «በአላህ በመልዕክተኛው እንዲህ ይደረግ» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (116-141) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከከል ዋና ዋናዎቹ**

1. ሙስሊሞች በአላህ ያመኑ ትክክለኛውን ሃይማኖት የተቀበሉ የአላህ መልዕክተኛን (ﷺ) ፈለግ የተከተሉ ምርጥ ሕዝቦች ከመሆናቸው ባሻገር ወደ መልካም የሚጠሩ ከመጥፎ ነገሮች የሚከለክሉ በመሆናቸው ከሁሉም የተሻሉና የበለጡ ሕዝቦች እንደሆኑ፤
2. ሙስሊሞች ሃይማኖታቸውን አጥብቀው ከያዙ የአላህ እርዳታ እንደማይለያቸው ድልም የነሱ መሆኑን፤
3. አይሁድ ላይም የተነገሩ ቁርአናዊ ትንታኔዎች ተፈፃሚ እንደሚሆኑ፤
4. ለአይሁዶች ውርደት መንስኤ የሆኑ የአይሁድ ወንጀሎች ምን ምን እንደሆኑ፤
5. ገንዘብም ሆነ ልጅ ከአላህ ቁጣ እንደማያድን፤
6. ከሓዲያን ከያዙት የክህደት መንገድ ሳይመለሱ ከሞቱ የገሀነም መሆናቸው የተጋገጠ መሆኑ፤
7. ኩፍር ኸይር ስራዎችን በሙሉ በማበላሸት ፋይዳ ቢስ እንደሚያደርጋቸው፤
8. ግንዛቤ ለማስተማር ምሳሌን መጠቀም የተሻለ መሆኑን እንደሚያስተምር፤
9. እውነተኛ ኢስላማዊ ጥሪ ያስተባበሉ ሰዎች ሁሉ መጨረሻቸው ኪሳራና ውድቀት መሆኑን፤
10. እምነት በልባቸው ሰርፆ የገባ ሰው ከቁርአናዊ አናቅፅ መመሪያ ጥቅሞችን እንደሚያገኙና አማኞች በዱንያም ሆነ በአኼራ ላይ የበላይ መሆናቸውን፤
11. የሰው ልጅ ህይወት መልካምም ሆነ መጥፎ ገፅታዎች ከዕለት ወደ ዕለት የሚፈራረቁበት ፍጡር መሆኑን፤

12. ችግሮች በሙስሊሞች ዘንድ የተስፋ መቁረጫ ሳይሆን እንዲማሩበትና የወደፊት ህይወታቸውን እንዲያስተካክሉ ንቃት ለመስጠት መሆኑን እንማራለን።

وَمَا مُحَمَّدٌ إِلَّا رَسُولٌ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِ ٱلرُّسُلُ ۚ أَفَإِيْن مَّاتَ أَوْ قُتِلَ ٱنقَلَبْتُمْ عَلَىٰٓ أَعْقَٰبِكُمْ ۚ وَمَن يَنقَلِبْ عَلَىٰ عَقِبَيْهِ فَلَن يَضُرَّ ٱللَّهَ شَيْـًٔا ۗ وَسَيَجْزِى ٱللَّهُ ٱلشَّٰكِرِينَ ﴿١٤٤﴾

**144.** መልዕክተኛችን ሙሐመድ ከበፊቱ ብዙ መልዕክተኞች በእርግጥ ያለፉ (የነበሩ) የሆነ መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም። ታዲያ እሱ ቢሞት ወይ በሰው ቢገደል ወደ ኋላችሁ ትገለበጣላችሁን? ወደ ኋላው የሚገለበጥ ሰው ሁሉ አላህን ምንም አይጎዳም። አላህ አመስጋኞቹን ተገቢዉን ይመነዳልና።

وَمَا كَانَ لِنَفْسٍ أَن تَمُوتَ إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ كِتَٰبًا مُّؤَجَّلًا ۗ وَمَن يُرِدْ ثَوَابَ ٱلدُّنْيَا نُؤْتِهِۦ مِنْهَا وَمَن يُرِدْ ثَوَابَ ٱلْءَاخِرَةِ نُؤْتِهِۦ مِنْهَا ۚ وَسَنَجْزِى ٱلشَّٰكِرِينَ ﴿١٤٥﴾

**145.** ማንኛዋም ነፍስ በአላህ ፍርድ (ፈቃድ) ቢሆን እንጂ ልትሞት (አትችልም) አይገባትም። የምትሞትበትም ጊዜ ቀድሞውኑ ተወስኖ ተፅፏል። የቅርቢቱን ዓለም ምንዳ የሚፈልግ ሰው ሁሉ ከእርሷ የወሰንለትን እንሰጠዋለን። የመጨረሻይቱን ዓለም ምንዳ የሚፈልግ ሰው ደግሞ ከእርሷ (የወሰንለትን) እንሰጠዋለን። አመስጋኞችንም በእርግጥ ተገቢውን እንመነዳለን።

وَكَأَيِّن مِّن نَّبِيٍّ قَٰتَلَ مَعَهُۥ رِبِّيُّونَ كَثِيرٌ فَمَا وَهَنُوا۟ لِمَآ أَصَابَهُمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَمَا ضَعُفُوا۟ وَمَا ٱسْتَكَانُوا۟ ۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلصَّٰبِرِينَ ﴿١٤٦﴾ وَمَا كَانَ قَوْلَهُمْ إِلَّآ أَن قَالُوا۟ رَبَّنَا ٱغْفِرْ لَنَا ذُنُوبَنَا وَإِسْرَافَنَا فِىٓ أَمْرِنَا وَثَبِّتْ أَقْدَامَنَا وَٱنصُرْنَا عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿١٤٧﴾ فَـَٔاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ ثَوَابَ ٱلدُّنْيَا وَحُسْنَ ثَوَابِ ٱلْءَاخِرَةِ ۗ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٤٨﴾

**146-148.** ከነብይም ብዙ ሊቃውንት ከእነርሱ ጋር ሆነው የተዋጉ ብዙ ናቸው። በአላህ መንገድ ለሚደርስባቸው ነገር ምንም አልፈሩም። አልደከሙም። ለጠላት አልተዋረዱም። አላህ ትዕግስተኞቹን ይወዳል። ንግግራቸውም ጌታችን ሆይ!ኃጢአቶቻችንንና በነገራችን ሁሉ ወሰን ማለፋችንን ማርልን። ጫማዎቻችንንም (ይዘታችንን) አደላድል። በከሐዲያን ሕዝቦች ላይ እርዳን ማለታቸው እንጂ ሌላ አልነበረም። አላህ የቅርቢቱን ዓለም ምንዳና የመጨረሻይቱን መልካም ምንዳ ሰጣቸው። አላህ በጎ አድራጊዎችን ሁሉ ይወዳልና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከ (144-148) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የኡሁድ ጦርነት ቀን ሙስሊሞች ሲሸነፉ አንዳንዶች ሙሐመድ (ﷺ) ተሸንፏል እጃችሁን ስጡ ወንድሞቻችሁ ናቸው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ሙሐመድ ከሞተስ ነብያችሁ በሞተበት መንገድ አትከተሉም በማለታቸው ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ዋሒዲ እና ኢብኑ ከሲር)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (142-148) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ድንጋጌዎችን ሳይለያዩ በያንዳንዱ ድንጋጌ መፈተን ከእምነት ግዴታዎች ጋር እንደሚጠቃለል፤
2. ነብዩ ታላቅ ክብር ያላቸው ቢሆንም ሰው እንደመሆናቸው እንደሚሞቱ ሁሉም ሙስሊም ይህን መረዳት እንደሚገባቸው፤
3. በጂሃድ ላይ መካፈል ከአላህ ተወስኖ የተሰጠን እድሜ እንደማይቀንሰው ሁሉ ከጂሃድ መሸሽም እንዲሁ እድሜን እንደማያራዝም፤
4. የስራ መልካምነትም ሆነ የሚያስገኘው ምንዳ የሚመዘነው፤ በኒያው ጥራት ልክ መሆኑን፤
5. እድሜ ልክ በእምነት ላይ ፅኑ መሆን አስፈላጊ ግዴታ መሆኑን፤
6. የደጋግ ሰዎችን ባህሪያት መከተል ተፈላጊ መሆኑን፤
7. በችግር ወቅት ዱዓ ማድረግ እንጂ መበሳጨትና መነጫነጭ አላህን ማማረር የተከለከለ መሆኑን ያስተምራል።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِن تُطِيعُواْ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يَرُدُّوكُمۡ عَلَىٰٓ أَعۡقَٰبِكُمۡ فَتَنقَلِبُواْ
خَٰسِرِينَ ﴿١٤٩﴾ بَلِ ٱللَّهُ مَوۡلَىٰكُمۡۖ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلنَّٰصِرِينَ ﴿١٥٠﴾ سَنُلۡقِي فِي قُلُوبِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ
ٱلرُّعۡبَ بِمَآ أَشۡرَكُواْ بِٱللَّهِ مَا لَمۡ يُنَزِّلۡ بِهِۦ سُلۡطَٰنٗاۖ وَمَأۡوَىٰهُمُ ٱلنَّارُۖ وَبِئۡسَ مَثۡوَى ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٥١﴾

**149-151.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በአላህ የካዱትን ሰዎች ባሏችሁ ሁሉ ብትታዘዙ ወደ ኋላችሁ ይመልሷችኋል። ከከሳሪዎቹም ትሆናላችሁ። ይልቁን አላህ ብቻ ረዳታችሁ ነው። እርሱ ከረዳቶች ሁሉ በላጭ ነውና።* በእነዚያ በአላህ በካዱት ሰዎች ልቦች ውስጥ አላህ በእሱ አስረጅ ያላወረደበትን ነገር በአላህ በማጋራታቸው ምክንያት ፍርሃትን እናደርጋለን። የመጨረሻ መኖሪያቸውም የገሀነም እሳት ናት። የበዳዮች መኖሪያ የሆነችው ገሀነምም መኖሪያነቷ ምን ትከፋ!

* አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ሰሙራህ ኢብኑ ጁንዱብ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከሰዎች መካከል ሙሽሪክ ከሆነ ሰው ጋር የሚገናኝ፤ የሚቀላቀል፤ የሚሰበሰብ፤ የሚኖርና ሀሳቡን ተቀብሎ ከእሱ ጋር አብሮ በመኖር ደስተኛ ከሆነ ይህ ሰው ልክ እንደ ሙሽሪኩ ነው»

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (151) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በኡሁድ ጦርነት ቀን አቡሱፊያንና አጋሮቹ ወደ መካ ሲመለሱ መሀል መንገድ ላይ እንደ ደረሱ ለምን ሳንጨርሳቸው ተመለስን በማለት ተፀፅተው ተመልሰው እንዲጨርሷቸው ስለወሰኑ አላህ በልቦቻቸው ይህ ነው ያልተባለ ፍርሀትና ስጋት ስላመጣባቸው ሳይፈፅሙት ቀሩ። ይህን ሁኔታ ለመግለፅ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

وَلَقَدْ صَدَقَكُمُ ٱللَّهُ وَعْدَهُۥٓ إِذْ تَحُسُّونَهُم بِإِذْنِهِۦ ۖ حَتَّىٰٓ إِذَا فَشِلْتُمْ وَتَنَٰزَعْتُمْ فِى ٱلْأَمْرِ
وَعَصَيْتُم مِّنۢ بَعْدِ مَآ أَرَىٰكُم مَّا تُحِبُّونَ ۚ مِنكُم مَّن يُرِيدُ ٱلدُّنْيَا وَمِنكُم مَّن يُرِيدُ ٱلْءَاخِرَةَ ۚ
ثُمَّ صَرَفَكُمْ عَنْهُمْ لِيَبْتَلِيَكُمْ ۖ وَلَقَدْ عَفَا عَنكُمْ ۗ وَٱللَّهُ ذُو فَضْلٍ عَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٥٢﴾

**152.** አላህ በፈቃዱ ጠላቶቻችሁን በምትጨፈጭፏቸው ጊዜ ቃልኪዳንን በእርግጥ አረጋገጠላችሁ። የምትወዱትንም ነገር ካሳያችሁ በኋላ በፈራችሁ ጊዜ፤ በትዕዛዙም በተጨቃጨቃችሁና ባመፃችሁም ጊዜ (እርዳታውን ከለከላችሁ)። ከናንተ ውስጥ ቅርቢቱን ዓለም የሚሻ ክፍል አለ። ከናንተም የመጨረሻውን አለም የሚፈልግ አለ። ከዚያ ሊሞክራችሁ ከእነርሱ አዞራችሁ። በእርግጥም ለእናንተ ይቅርታ አደረገላችሁ። አላህ ሁልጊዜም በምዕመናን ላይ የችሮታ ባለቤት ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (152) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- እነዚህ አናቅፅ ደግሞ የሙስሊሙን ሀይል በኡሁድ ዘመቻ የመሩት ነብዩ (ﷺ) ከዘመቻ ሲመለሱ አንዳንድ ሙስሊሞች በኡሁድ ዘመቻ በሙስሊሞች ላይ የደረሰውን ሽንፈት እያስታወሱ ለምን ተሸነፍን? እንዴትስ ሽንፈት ተከሰተ? እያሉ በመናገራቸው አላህ እነዚህን አናቅፅ አወረደ። (ዋሒዲ፤ ቁርጡቢና ኢብኑ ከሲር)

۞ إِذْ تُصْعِدُونَ وَلَا تَلْوُۥنَ عَلَىٰٓ أَحَدٍ وَٱلرَّسُولُ يَدْعُوكُمْ فِىٓ أُخْرَىٰكُمْ فَأَثَٰبَكُمْ غَمًّۢا بِغَمٍّ
لِّكَيْلَا تَحْزَنُوا۟ عَلَىٰ مَا فَاتَكُمْ وَلَا مَآ أَصَٰبَكُمْ ۗ وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿١٥٣﴾ ثُمَّ أَنزَلَ
عَلَيْكُم مِّنۢ بَعْدِ ٱلْغَمِّ أَمَنَةً نُّعَاسًا يَغْشَىٰ طَآئِفَةً مِّنكُمْ ۖ وَطَآئِفَةٌ قَدْ أَهَمَّتْهُمْ أَنفُسُهُمْ
يَظُنُّونَ بِٱللَّهِ غَيْرَ ٱلْحَقِّ ظَنَّ ٱلْجَٰهِلِيَّةِ ۖ يَقُولُونَ هَل لَّنَا مِنَ ٱلْأَمْرِ مِن شَىْءٍ ۗ قُلْ إِنَّ ٱلْأَمْرَ
كُلَّهُۥ لِلَّهِ ۗ يُخْفُونَ فِىٓ أَنفُسِهِم مَّا لَا يُبْدُونَ لَكَ ۖ يَقُولُونَ لَوْ كَانَ لَنَا مِنَ ٱلْأَمْرِ شَىْءٌ مَّا قُتِلْنَا
هَٰهُنَا ۗ قُل لَّوْ كُنتُمْ فِى بُيُوتِكُمْ لَبَرَزَ ٱلَّذِينَ كُتِبَ عَلَيْهِمُ ٱلْقَتْلُ إِلَىٰ مَضَاجِعِهِمْ ۖ وَلِيَبْتَلِىَ
ٱللَّهُ مَا فِى صُدُورِكُمْ وَلِيُمَحِّصَ مَا فِى قُلُوبِكُمْ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿١٥٤﴾

**153-154.** (የመልዕክተኛችን ሙሐመድ ባልደረቦች ሆይ!) መልዕክተኛው ከኋላችሁ ሁኖ እየጠራችሁ የማትዞሩ ሆናችሁ በርቀት በምትሸሹ ጊዜ (የሆነውን አስታውሱ)። ባመለጣችሁና በደረሰባችሁም ነገር አለማዘንን ሊያስተምራችሁ በሀሳብ ላይ ሀሳብም አደረሰባችሁ። አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው። ከዚያ ከጭንቅ በኋላ ፀጥታን ከናንተ ከፊሎችን የሚሸፍንን እንቅልፍ በእናንተ ላይ አወረደ። ከፊሎችም ነፍሶቻቸው በእርግጥ አሳሰቧቸው። እውነት ያልሆነውን የመሀይምነትን መጠራጠር በአላህ ላይ ይጠራጠራሉ።

በነገሩ ላይ ምንም የመወሰን መብት የለንም ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመወሰን መብት የአላህ ብቻ ነው በላቸው። ላንተ ግልጽ የማያደርጉትን በልቦቻቸው ውስጥ ይደብቃሉ። የመወሰን መብት ቢኖረን ኖሮ በዚህ ቦታ ላይ ባልተገደልን ነበር ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በቤታችሁ ውስጥ በሆናችሁም ኖሮ እነዚያ በእነርሱ ላይ መገደል የተፃፈባቸው ወደ የመውደቂያቸው በወጡ ነበር በላቸው። አላህ ፍርዱን ሊፈፅምና በደረቶቻችሁም ውስጥ ያለውን ሊፈትን በልቦቻችሁም ውስጥ ያለውን ነገር ሊገልፅ (ይህንን ሰራ)። አላህ በደረቶች ውስጥ ያለውን ሁሉ ነገር ሳይቀር አዋቂ ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (154) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዙበይር ኢብኑ አልአዋም ሲናገሩ የኡሁድ ዘመቻ እለት ፍርሃቱ በጣም ጠንክሮ በነበረበት ሰዓት አላህ እንቅልፍ ለቀቀብንና ሁላችንም አገጫችን ደረታችን ላይ ወደቀ እኔም በእንቅልፍ ልቤ ሙትዒብ ብን ቁሸይር የተባለ ሰው የሆነ ነገር ላይ ብንሆን ኖሮ እዚህ አንገደልም ነበር እያለ ሲናገር አባበሉን በቃሌ ያዝኳት አላህም ይህን አስመልክቶ ይህን አንቀፅ አወረደ ብለዋል። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱلَّذِينَ تَوَلَّوۡاْ مِنكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡتَقَى ٱلۡجَمۡعَانِ إِنَّمَا ٱسۡتَزَلَّهُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ بِبَعۡضِ مَا كَسَبُواْۖ
وَلَقَدۡ عَفَا ٱللَّهُ عَنۡهُمۡۗ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ حَلِيمٞ ١٥٥

**155.** የመልዕክተኛችን ባልደረቦች ሆይ! እነዚያ ሁለቱ ቡድኖች በተገናኙ ቀን ከናንተ የሸሹት ሰዎች በዚያ በሰሩት ክፍል ምክንያት ያሳሳታቸው ሰይጣን ነው። አላህ ከእነርሱ በእርግጥ ይቅር አለ። አላህ መሀሪና ለቅጣት የማይቸኩል ታጋሽ ነውና።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَكُونُواْ كَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَقَالُواْ لِإِخۡوَٰنِهِمۡ إِذَا ضَرَبُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ
أَوۡ كَانُواْ غُزّٗى لَّوۡ كَانُواْ عِندَنَا مَا مَاتُواْ وَمَا قُتِلُواْ لِيَجۡعَلَ ٱللَّهُ ذَٰلِكَ حَسۡرَةٗ فِي قُلُوبِهِمۡۗ
وَٱللَّهُ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ١٥٦

**156.** (እናንተ በትክክል በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እነደነዚያ በአላህ እንደካዱትና ስለ ወንድሞቻቸው በምድር ላይ በተጓዙና ወይም ዘማቾች በሆኑ ጊዜ እኛ ዘንድ በነበሩ ኖሮ ባልሞቱ ባልተገደሉም ነበር እንደሚሉት ሰዎች አትሁኑ። አላህ በልቦቻቸው ውስጥ ፀፀት ያደርግባቸው ዘንድ (ይህንን አሉ)። አላህ የፈለገውን ሕያው ያደርጋል። የፈለገውን ይገድላልም። አላህ የምትሰሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነው።

وَلَئِن قُتِلْتُمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ أَوْ مُتُّمْ لَمَغْفِرَةٌ مِّنَ ٱللَّهِ وَرَحْمَةٌ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ ﴿١٥٧﴾
وَلَئِن مُّتُّمْ أَوْ قُتِلْتُمْ لَإِلَى ٱللَّهِ تُحْشَرُونَ ﴿١٥٨﴾

**157-158.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በአላህ መንገድ ላይ ስትዋጉ ብትገደሉ ወይም ብትሞቱ ከአላህ የሆነው ምህረትና እዝነት እነርሱ ከሚሰበስቡት ሀብት ሁሉ የእናንተ ምንዳ በላጭ ነው። በጂሃድ ብትሞቱ ወይም ብትገደሉ ወደ አላህ ብቻ ትሰበሰባላችሁ።

**ከዒምራን ቤተሰቦች ከአንቀፅ ምዕራፍ (149-158) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን እና የረሱልን ትዕዛዝ መጣስ መጨረሻው የከፋ መሆኑን፤
2. በተቻለ አቅም የካፊሮችን ትዕዛዝ አለመፈፀም ተገቢ መሆኑን፤
3. ድል አድራጊነትን ከአላህ ውጪ ከሌላ አካል የፈለገ ሰው አላህ ውርደትን እንደሚከናንበው፤
4. አላህ ምእመናን ድልን ማቀዳጀቱና ከሓዲያንን ደግሞ በፍርሀት ማርበድበዱን፤
5. ያለ ማስረጃ የሚደረግ ክርክር በሙሉ ውድቅ ስለመሆኑ፤
6. አላህ ለቅን ወዳጅ ባሪያዎቹ ውስጣዊና ውጫዊ ሰላም የሚለግስ መሆኑን፤
7. አመፀኛ ጠላቶቹንም ለጉዳት እንደሚዳርግ፤
8. የአላህ ውሳኔዎችና ክንውኖች በሙሉ ለሁላችንም ግልፅ ባይሆንም ምክኒያታዊ መሆናቸዉን፤
9. ወንጀል ለሌላ ተጨማሪ ወንጀል የሚጋብዝ መሆኑን፤፤
10. ባለፈ ነገር መፀፀትም ሌላ ፀፀትን የሚያስከትል መሆኑን፤
11. የአላህን ሃይማኖት ከፋ ለማድረግ ሕይወትን አሳልፎ መስጠት ከዱንያና ከውስጧም ካሉ ፀጋዎች በሙሉ እንደሚበልጥ፤
12. በውስጣዊም ሆነ በውጫዊ መንፈሳዊ ተግባራት ካፊሮችን መመሳሰል የተከለከለ መሆኑን፤
13. ሁሉም ነገር ሊሆን የሚችለው በአላህ ውሳኔ ብቻ መሆኑን፤
14. የቀደር እምነት ለሁሉም አስፈላጊ መሆኑን እንማራለን።

فَبِمَا رَحْمَةٍ مِّنَ ٱللَّهِ لِنتَ لَهُمْ ۖ وَلَوْ كُنتَ فَظًّا غَلِيظَ ٱلْقَلْبِ لَٱنفَضُّوا۟ مِنْ حَوْلِكَ ۖ فَٱعْفُ عَنْهُمْ وَٱسْتَغْفِرْ لَهُمْ وَشَاوِرْهُمْ فِى ٱلْأَمْرِ ۖ فَإِذَا عَزَمْتَ فَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلْمُتَوَكِّلِينَ ﴿١٥٩﴾ إِن يَنصُرْكُمُ ٱللَّهُ فَلَا غَالِبَ لَكُمْ ۖ وَإِن يَخْذُلْكُمْ فَمَن ذَا ٱلَّذِى يَنصُرُكُم مِّنۢ بَعْدِهِۦ ۗ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ﴿١٦٠﴾

**159-160.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ችሮታ ለዘብክላቸው። አመለ መጥፎና ልበ ደረቅ በሆንክ ኖሮ ከአጠገብህ በተበተኑ ነበር። ከእነርሱም ጥፋት ይቅር በል። ለእነርሱም ከአላህ ምህረትን ለምንላቸው። በሁሉም ነገር ላይ አማክራቸው። ከዚያ ቁርጥ ሀሳብ ባደረግህ ጊዜ በአላህ ላይ ብቻ ተመካ። አላህ በእርሱ ላይ ብቻ ተመኪዎችን ይወዳልና። ሙስሊሞች ሆይ! አላህ ከረዳችሁ እናንተን አሸናፊ ማንም የለም። እርሱ ካዋረዳችሁ ደግሞ ከእርሱ ማዋረድ በኋላ የሚረዳችሁ ያ ማን ነው? እናም በአላህ ላይ ብቻ አማኞች ይመኩ።

وَمَا كَانَ لِنَبِيٍّ أَن يَغُلَّ ۚ وَمَن يَغْلُلْ يَأْتِ بِمَا غَلَّ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ ۚ ثُمَّ تُوَفَّىٰ كُلُّ نَفْسٍ مَّا كَسَبَتْ
وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿١٦١﴾ أَفَمَنِ ٱتَّبَعَ رِضْوَٰنَ ٱللَّهِ كَمَنۢ بَآءَ بِسَخَطٍ مِّنَ ٱللَّهِ وَمَأْوَىٰهُ جَهَنَّمُ ۚ
وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿١٦٢﴾ هُمْ دَرَجَـٰتٌ عِندَ ٱللَّهِ ۗ وَٱللَّهُ بَصِيرٌۢ بِمَا يَعْمَلُونَ ﴿١٦٣﴾

**161-163.** ለነብዩም ቢሆን የምርኮን ገንዘብ መደበቅ አይገባውም። የምርኮን ገንዘብ የሚደብቅ ሰው ሁሉ በትንሳኤ ቀን የደበቀውን ነገር ተሸክሞ ይመጣል። ከዚያ ነፍስ ሁሉ የሰራዋን ዋጋ ትመነዳለች። እነርሱም ቅንጣትም ያህል አይበደሉም። የአላህን ውዴታ የተከተለ ሰው ሁሉ የአላህ ቁጣ እንደተፈረደበትና መኖሪያው ገሀነም እንደሆነበት ሰው ነውን? ገሀነም ማረፊያነቱ እጅግ የከፋ ነው!፣ ሁሉም በአላህ ዘንድ ባለ ልዩ ልዩ ደረጃዎች ናቸው። አላህ የሚሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (161) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የበድር ዘመቻ ዕለት ሙስሊሞች አያሌ ንብረቶችን ከሙሽሪኮች ሀይል በምርኮ አግኝተዋል። እናም ከዚህ የምርኮ ንብረቶች ውስጥ አንዲት ጋቢ በመጥፋቷ ነብዩ (ﷺ) ወስደዋት ይሆናል በማለት አንዳንድ ሰዎች ስለተናገሩ ንግግራቸው እና ጥርጣሬያቸው ተገቢ ያልነበረ በመሆኑና ይህ ግምታቸው የተሳሳተ መሆኑን ለማስረዳት እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። (ቲርሚዚ፣ ጦበሪ እና ዋሒዲ)

لَقَدْ مَنَّ ٱللَّهُ عَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ إِذْ بَعَثَ فِيهِمْ رَسُولًا مِّنْ أَنفُسِهِمْ يَتْلُوا۟ عَلَيْهِمْ ءَايَـٰتِهِۦ
وَيُزَكِّيهِمْ وَيُعَلِّمُهُمُ ٱلْكِتَـٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَإِن كَانُوا۟ مِن قَبْلُ لَفِى ضَلَـٰلٍ مُّبِينٍ ﴿١٦٤﴾

**164.** አላህ በአማኞች ላይ ከጎሳቸው የሆነን፤ በእነርሱም ላይ አንቀፆችን የሚያነብ፣ (ከርክሰት) የሚያጠራቸው፣ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውን መልዕክተኛ በውስጣቸው በላከ ጊዜ በእርግጥ ለገሰላቸው። እነርሱም ከዚያ በፊት ግልፅ ስህተት ውስጥ ነበሩ።

أَوَلَمَّآ أَصَـٰبَتْكُم مُّصِيبَةٌ قَدْ أَصَبْتُم مِّثْلَيْهَا قُلْتُمْ أَنَّىٰ هَـٰذَا ۖ
قُلْ هُوَ مِنْ عِندِ أَنفُسِكُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿١٦٥﴾

**165.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ በእርግጥ ሁለት እጥፍ ያደረሳችሁትን ጥቃት ግማሽ በአገኛችሁ (በደረሰባችሁ) ጊዜ ይህ (ጥቃት) ከየት ነው የመጣብን አላችሁን? እርሱ ከነፍሶቻችሁ ዘንድ ነው። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና በላቸው።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (165) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ የተፍሲር ዐሊሞች በኡሁድ ጦርነት በሙስሊሞች ላይ በደረሰው ሽንፈት ምክንያት ነው። የወረደው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ቢእርመዓነህ በተባለች ቦታ ላይ ሰማእት በሆኑት ሙስሊሞች ምክንያት ነው የወረደው ይላሉ። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَمَآ أَصَٰبَكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡتَقَى ٱلۡجَمۡعَانِ فَبِإِذۡنِ ٱللَّهِ وَلِيَعۡلَمَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١٦٦ وَلِيَعۡلَمَ ٱلَّذِينَ نَافَقُواْۚ وَقِيلَ
لَهُمۡ تَعَالَوۡاْ قَٰتِلُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ أَوِ ٱدۡفَعُواْۖ قَالُواْ لَوۡ نَعۡلَمُ قِتَالٗا لَّٱتَّبَعۡنَٰكُمۡۗ هُمۡ لِلۡكُفۡرِ يَوۡمَئِذٍ
أَقۡرَبُ مِنۡهُمۡ لِلۡإِيمَٰنِۚ يَقُولُونَ بِأَفۡوَٰهِهِم مَّا لَيۡسَ فِي قُلُوبِهِمۡۚ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا يَكۡتُمُونَ ١٦٧

**166-167.** ሁለት ቡድኖች በተጋጠሙ ቀን የደረሰባችሁ በአላህ ፈቃድ ብቻ ነው። የምዕመናንን አቋም ሊፈትንና ማንነታቸውን ሊገልፅ ነው። እነዚያን የነፈቁትንና ኑ በአላህ መንገድ ተጋደሉ ወይም ተከላከሉ የተባሉትን ሊገልፅ ነው (ይህን ያደረገው)። መናፍቃን ውጊያ መኖሩን ብናውቅ ኖሮ በተከተልናችሁ ነበር አሉ። እነርሱም ያን ጊዜ ከእምነት ይልቅ ወደ ክህደት የቀረቡ ናቸው። በልቦቻቸው የሌለውን በአፎቻቸው ይናገራሉ። አላህም የሚደብቁትን ሁሉ አዋቂ ነው።

ٱلَّذِينَ قَالُواْ لِإِخۡوَٰنِهِمۡ وَقَعَدُواْ لَوۡ أَطَاعُونَا مَا قُتِلُواْۗ قُلۡ فَٱدۡرَءُواْ عَنۡ أَنفُسِكُمُ ٱلۡمَوۡتَ إِن
كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٦٨ وَلَا تَحۡسَبَنَّ ٱلَّذِينَ قُتِلُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ أَمۡوَٰتَۢاۚ بَلۡ أَحۡيَآءٌ عِندَ رَبِّهِمۡ
يُرۡزَقُونَ ١٦٩ فَرِحِينَ بِمَآ ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦ وَيَسۡتَبۡشِرُونَ بِٱلَّذِينَ لَمۡ يَلۡحَقُواْ بِهِم مِّنۡ
خَلۡفِهِمۡ أَلَّا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ١٧٠ ۞ يَسۡتَبۡشِرُونَ بِنِعۡمَةٖ مِّنَ ٱللَّهِ وَفَضۡلٖ وَأَنَّ
ٱللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجۡرَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١٧١

**168-171.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚህ ከትግል ወደ ኋላ የቀሩ ሲሆኑ ለወንድሞቻቸው፤ እኛን በታዘዙን ኖሮ ባልተገደሉ ነበር ያሉ ናቸው። እናም እውነተኞች ከሆናችሁ እስቲ ከነፍሶቻችሁ ላይ ሞትን ገፍትሩ በሏቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን በአላህ መንገድ የተገደሉትን ሰማዕታት ሙታን አድርገህ አትገምታቸው። በእርግጥ እነርሱ ጌታቸው ዘንድ ሕያውያን ናቸውና። ከጌታቸው ዘንድ ሲሳይ ይለገሳሉ። አላህ ከችሮታው በሰጣቸው ነገር ተደሳቾች ሲሆኑ ይመገባሉ። በእነዚያም ከኋላቸው ገና ባልተከተሉት ክፍሎች በእነርሱ ላይ ምን ይደርስብናል ብለው ፍርሃት ባለመኖሩና ምንም ያመልጠናል ብለው የማያዝኑ በመሆናቸው ይደሰታሉ በአላህ ፀጋ፤ ችሮታና የምዕመናንን ምንዳ የማያጠፋ በመሆኑ ይደሰታሉ።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (169) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ እንደተናገሩት በኡሁድ ጦርነት ዕለት የተሰውት ሙስሊሞች ሩሃቸውን አላህ በአረንጓዴ ወፍ ውስጥ አድርጎ በየዕለቱ በጀነት ወንዞች እንደሚያስደስታቸው፤ ከጀነት አትክልቶች ፍሬ እንደሚመግባቸውና በአርሽ ጥላ ስር በተቀመጠ የወርቅ ቀንዲል የሚያርፉ መሆናቸውን ሲያረጋግጡ ይህ ሁኔታ ለወንድሞቻቸው በምን መልኩ እንደሚደርሳቸውና ጂሃድ ላይ እንዲጠናከሩና እንደይሰንፉ በመጨነቅ ላይ ያሉ አላህ እኔ አደርሳችኋለሁ በማለት ይህን አንቀፅ አወረደ። (አቡ ዳውድ፤ አህመድ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ٱلَّذِينَ ٱسْتَجَابُوا۟ لِلَّهِ وَٱلرَّسُولِ مِنۢ بَعْدِ مَآ أَصَابَهُمُ ٱلْقَرْحُ ۚ لِلَّذِينَ أَحْسَنُوا۟ مِنْهُمْ وَٱتَّقَوْا۟
أَجْرٌ عَظِيمٌ ﴿١٧٢﴾ ٱلَّذِينَ قَالَ لَهُمُ ٱلنَّاسُ إِنَّ ٱلنَّاسَ قَدْ جَمَعُوا۟ لَكُمْ فَٱخْشَوْهُمْ فَزَادَهُمْ
إِيمَٰنًا وَقَالُوا۟ حَسْبُنَا ٱللَّهُ وَنِعْمَ ٱلْوَكِيلُ ﴿١٧٣﴾ فَٱنقَلَبُوا۟ بِنِعْمَةٍ مِّنَ ٱللَّهِ وَفَضْلٍ لَّمْ يَمْسَسْهُمْ
سُوٓءٌ وَٱتَّبَعُوا۟ رِضْوَٰنَ ٱللَّهِ ۗ وَٱللَّهُ ذُو فَضْلٍ عَظِيمٍ ﴿١٧٤﴾ إِنَّمَا ذَٰلِكُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ يُخَوِّفُ
أَوْلِيَآءَهُۥ فَلَا تَخَافُوهُمْ وَخَافُونِ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿١٧٥﴾

**172-175.** እነዚያን የመቁሰል አደጋ ከደረሰባቸው በኋላ ለአላህና ለመልዕክተኛው የታዘዙ ሰዎች ከእነርሱ መካከል በጎ ተግባርን ለሰሩና አላህን ለተጠነቀቁት ክፍሎች ሁሉ ታላቅ ምንዳ አለላቸው። እነዚያ ማለት ጠላቶች ለእናንተ ጦርን እንደገና አከማችተዋልና ፍሯቸው ያሏቸውና ይህም እምነትን በእምነት የጨመረላቸው ቃላቸውም በቂያችንም አላህ ነው፤ እርሱም ምን ያምር መጠጊያ፣ * ነው ያሉ ናቸው። የአላህን ፀጋና ችሮታ ይዘው ምንም ክፉ ነገር ሳይነካቸው በሰላም ተመለሱ። የአላህን ውዴታ ተከተሉ። አላህ የታላቅ የችሮታ ባለቤት ነውና። ይህ የሚያስፈራራችሁ ሰይጣን ብቻ ነው። ከወዳጆቹ ጥቃት ያስፈራራችኋል። አማኞች የሰይጣንን ወዳጅ አትፍሯቸው። ትክክለኛ ምዕመናን ከሆናችሁ እኔን ብቻ ፍሩኝ።

✶ (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ፡- «በቂያችንም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ! የሚለውን ኢብራሂም እሳት ውስጥ ሲወረወሩ እንዲሁም ሙሐመድ ሙሽሪኮች «ሰዎች ለናንተ ጦርን አከማችተዋልና ፍሩዋቸው ያሉዋቸውና ይህም እምነት የጨመረላቸው በቂያችን አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ ያሉ ናቸው» ሲሉ የተናሩት ነው ብለዋል።

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላለፉት«ኢብራሂም እሳት ውስጥ ሲወረውሩ የተናገሩት የመጨረሻ ቃል (ሃስቡን አላህ ወኒዕመል ወኪል) «በቂም አላህ ነው ምን ያምርም መጠጊያ» የሚለው ነበር።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (172) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከኡሁድ ዘመቻ በኋላ ሙሽሪኮች ወደ ሀገራቸው ሲመለሱ ለሙስሊሞች ቅስቀሳ ያደርጋሉ። ከዚያ ሰባ ሰዎች ብቻ አብረዋቸው ተነስተው ሀሳቡን ይቀበላሉ። አቡ ሱፍያን በመንገድ ላይ የበኒ ሁዝአን ነጋዴዎች አግኝቶ ሙሐመድ ስለ እኔ ከጠየቃችሁ ብዙ ሕዝብ አብሮኝ እንዳለ ንገሩት ብሎ ልኮ ነበር እና ነጋዴዎቹም

ነብዩን ሰያገናኟቸው አቡ ሱፍያንን እያሳደዱ መሆናቸውን ሲያዩ «አቡ ሱፍያን እኮ ብዙ ሕዝብ ነው አብሮት ያለው» በማለት መልዕክታቸውን ይነግራሉ። ነብዩም (ﷺ) ሆኑ አብረዋቸው የነበሩ ሙስሊሞች ስጋት ሳያድርባቸው አቡ ሱፍንን ማሳደዳቸውን ቀጠሉ። ሆኖም አቡ ሱፍያን ጠንክሮ በመገስገሱ ሳይደርሱበት ሰራዊቱን በሰላም ይዞ መካ ገባ። ይህ የቁርኣን አንቀፅ የወረደው ይህን ታሪክ ምክንያት በማድረግ ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (173) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በኡሁድ ዘመቻ ዕለት ከደረሰው አሰቃቂ ክስተት በኋላ ነብዩ (ﷺ) ለሙስሊሞች «ለአላህ ዲን የሚታገል ጀግና ጠላትን ተከትሎ የሚያሳድድ የለም። ይህ እኮ ለሞራሉም ሆነ ለስሙ ጥሩ ነበር» ሲሉ የተወሰኑ ሰዎች ይህን ሰምተው ተከታትለው ጠላትን ሲያፈላልጉና ዙልሁለይፋ ሲደርሱ ሰዎች እየመጡ አቡ ሱፍያን ሰራዊቱን ይዞ ወደ እናንተ ሊዘምትና ሊዞርባችሁ ነው ሲሏቸው «ለእኛም አላህ አለን በቂያችንም እሱ ብቻ ነው» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (159-175) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩ እጅግ ምርጥና ተወዳጅ ባህሪ እንደነበራቸው፤
2. ምክክር ማድረግ ከተወዳጅ የኢስላም መገለጫዎች አንዱ መሆኑን፤
3. በየትኛውም ተግባራችን ላይ የአላህ ውዴታን መፈለግ ግዴታ መሆኑን፤
4. ችግሮችና መከራዎች የወንጀል ውጤቶች መሆናቸውን፤
5. በአለም ላይ ዕለት በዕለት የሚከሰቱ ክንውኖች በሙሉ አላህ ከመከሰታቸው ቀድሞ የሚያውቃቸው ነገሮች እንደሆኑ፤
6. ጥንቃቄ ማድረጉ አስፈላጊ ቢሆንም የአላህ ውሳኔ የተላለፈበትን ነገር ጥንቃቄ ሊያድነውና ሊገድበው እንደማይችል፤
7. የነብዩ (ﷺ) ጓዶች ከሌሎች ሰዎች በተለየ መልኩ የተሰጣቸው ታላቅ ክብር፤
8. «አላህ በቂያችን ነው በእርሱ መመካት አማረ» (ሀስቡነላህ ወኒዕመል ወኪል) በማለት በችግር ጊዜ አላህን ማስታወስና በእርሱ መመካት እጅግ ተወዳጅና አጅሩም የበዛና የነብያት ፈለግ መሆኑን፤
9. ሰይጣን ሙስሊሞችን ለማስፈራራትና ለማርበትበት መጠነ ሰፊ ሙከራዎች እንደሚያደርግ፤
10. ከሁለት አስቸጋሪ ነገሮች መካከል አንዱን ለመፈፀም አማራጭ ከጠፋ አነስተኛውን ጥፋት መፈፀም፤ እንዲሁም ከሁለት ጥቅሞች በአንዱ ላይ የተማረጠ ሰው የበለጠውን መምረጥ አለበት፤
11. የሰራተኛን የአገልግሎት ክፍያ ልጅን በመዳርም እንኳ ቢሆን መዋዋል እንደሚቻል እንማራለን።

وَلَا يَحْزُنكَ ٱلَّذِينَ يُسَٰرِعُونَ فِى ٱلْكُفْرِ ۚ إِنَّهُمْ لَن يَضُرُّوا۟ ٱللَّهَ شَيْـًٔا ۗ يُرِيدُ ٱللَّهُ أَلَّا يَجْعَلَ
لَهُمْ حَظًّا فِى ٱلْءَاخِرَةِ ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ عَظِيمٌ ﴿١٧٦﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ ٱشْتَرَوُا۟ ٱلْكُفْرَ بِٱلْإِيمَٰنِ لَن
يَضُرُّوا۟ ٱللَّهَ شَيْـًٔا ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿١٧٧﴾ وَلَا يَحْسَبَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ أَنَّمَا نُمْلِى لَهُمْ خَيْرٌ
لِّأَنفُسِهِمْ ۚ إِنَّمَا نُمْلِى لَهُمْ لِيَزْدَادُوٓا۟ إِثْمًا ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ مُّهِينٌ ﴿١٧٨﴾

**176-178.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የእነዚያ ወደ ክህደት የሚቻኮሉ ሰዎች አድራጎት (ተግባር) አያሳዝንህ። እነርሱ ፈፅሞ አላህን በምንም አይጎዱትምና። አላህ በመጨረሻይቱ ዓለም ለእነርሱ እድልን ላያደርግ ይሻልና። ለእነርሱም ታላቅ ቅጣት አለባቸው። እነዚያ ክህደትን በእምነት የለወጡ ክፍሎች ሁሉ አላህን በምንም ነገር ፈፅሞ አይጎዱትም። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ እነርሱን ማዘግየታችንን ለነፍሶቻችን ደግ ነገር ነው ብለው አያስቡ። እነርሱን የምናዘገያቸው ኃጢአትን እንዲጨምሩ ብቻ ነውና። ለእነርሱም አዋራጅ ቅጣት አለባቸው።

مَّا كَانَ ٱللَّهُ لِيَذَرَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ عَلَىٰ مَآ أَنتُمۡ عَلَيۡهِ حَتَّىٰ يَمِيزَ ٱلۡخَبِيثَ مِنَ ٱلطَّيِّبِۗ وَمَا كَانَ
ٱللَّهُ لِيُطۡلِعَكُمۡ عَلَى ٱلۡغَيۡبِ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَجۡتَبِي مِن رُّسُلِهِۦ مَن يَشَآءُۖ فَـَٔامِنُواْ بِٱللَّهِ
وَرُسُلِهِۦۚ وَإِن تُؤۡمِنُواْ وَتَتَّقُواْ فَلَكُمۡ أَجۡرٌ عَظِيمٞ ١٧٩

**179.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) አላህ መጥፎውን ከመልካሙ እስከሚለይ ድረስ ምዕመናንን አሁን እናንተ ባላችሁበት ሁኔታ ላይ የሚተዋቸው አይደለም። አላህ ሩቁን ነገር ሁሉ የሚያሳውቃችሁ አይደለም። ግን አላህ ከመልዕክተኞቹ የሚሻውን ይመርጣል። እናም በአላህና በመልዕክተኞቹ ሁሉ እመኑ። ብታምኑና ብትጠነቀቁ ለእናንተ ታላቅ ምንዳ አለላችሁ።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (179) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙስሊሞች ትክክለኛ አማኝንና አስመሳይ አስመሳዮችን የሚለዩበት ምልክት እንዲሰጣቸው ነብዩን (ﷺ) ስለጠየቁ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ቁርጡቢ)

وَلَا يَحۡسَبَنَّ ٱلَّذِينَ يَبۡخَلُونَ بِمَآ ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦ هُوَ خَيۡرٗا لَّهُمۖ بَلۡ هُوَ شَرّٞ لَّهُمۡۖ سَيُطَوَّقُونَ
مَا بَخِلُواْ بِهِۦ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۗ وَلِلَّهِ مِيرَٰثُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ١٨٠

**180.** እነዚያ አላህ ከችሮታው ከሰጣቸው ገንዘብ የሚነፍጉ ሰዎች ሁሉ ንፉግነት ደግ ተግባር አይምሰላቸው። ይልቁንም እርሱ ለእነርሱ መጥፎ ባህሪ ነው። ያንን በእርሱ የነፈጉበት ገንዘብ በትንሳኤ ቀን* (እባብ ሆኖ በአንገታቸው) ይጠለቃሉ። የሰማያትና የምድር ውርስ ለአላህ ብቻ ነው። አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና።

✷ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ገንዘብ ሰጥቶት ከገንዘቡ ላይ ዘካህ የማይሰጥ ሰው የትንሳኤ ቀን ገንዘቡ እንደ ፀጉር አልባና ሁለት መርዛማ እጢዎች እንዳሉት ወንድ እባብ ወደ እርሱ ይመጣና በአንገቱ ላይ ተጠምጥሞ ሁለት ጉንጮቹን በመሳም «እኔ ገንዘብህ ነኝ ሀብትህ ነኝ ይለዋል» ካሉ በኋላ ይህን አንቀፅ አነበቡ። «እነዚያም አላህ ችሮታው በሰጣቸው ገንዘብ የሚነፍጉ እርሱ ከነሱ ደግ አይምሰላቸው፤ ይልቁንም እርሱ ለነሱ መጥፎ ነው፤ ያንን በርሱ የነፈጉበትን በትንሳኤ ቀን እባብ ሆኖ ይጠቀለልባቸዋል። የሰማያትና የምድር ውርስ ለአላህ ብቻ ነው፤ አላህም በሚሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው» (ኣሊ- ዒምራን፡ **180**)

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (**180**) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ብዙ የተፍሲር ዐሊሞች እንደሚሉት «ይህ አንቀፅ የወረደው ዘካን አንሰጥም ባሉ ሰዎች ምክንያት ነው ሲሉ» ሌሎች ደግሞ «የነብዩን (ﷺ) ንፁህ ታሪክ በለዋወጡና ባበላሹ የአይሁድ ምሁራን ምክንያት ነው የወረደው» ይላሉ። (ኢብኑል-ጀውዚ)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (176-180) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ የሰዎችን ወንጀል እያየ በዝምታ መታዘቡና እርምጃ አለመወሰዱ ሊያዘናጋን እንደማይገባ፤
2. ፈተና ትክክለኛ አማኞችን ከከሓዲያን ለመለየት የሚያስችል ጠቃሚ ነገር መሆኑን፤
3. የተሰወሩ ነገሮችን (ገይብ) የማወቅ ስልጣንና መብት ያለው አላህ ብቻ መሆኑን፤
4. አላህን መፍራት ጀነትን እንደሚያጎናፅፍ፤
5. ገንዘብ ኖሮት በገንዘብ የሚፈፀሙ ግዴታዎችን ያልተወጣ በቂያማ ዕለት በገንዘቡ እንደሚቀጣበት፤
6. ስስታምነት (ንፉግነት) ለባለቤቱም ቢሆን የማይበጅ መጥፎ ባህሪይ መሆኑን እንማራለን።

لَّقَدْ سَمِعَ ٱللَّهُ قَوْلَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓا۟ إِنَّ ٱللَّهَ فَقِيرٌ وَنَحْنُ أَغْنِيَآءُ ۘ سَنَكْتُبُ مَا قَالُوا۟ وَقَتْلَهُمُ
ٱلْأَنۢبِيَآءَ بِغَيْرِ حَقٍّ وَنَقُولُ ذُوقُوا۟ عَذَابَ ٱلْحَرِيقِ ١٨١ ذَٰلِكَ بِمَا قَدَّمَتْ أَيْدِيكُمْ وَأَنَّ
ٱللَّهَ لَيْسَ بِظَلَّامٍ لِّلْعَبِيدِ ١٨٢ ٱلَّذِينَ قَالُوٓا۟ إِنَّ ٱللَّهَ عَهِدَ إِلَيْنَآ أَلَّا نُؤْمِنَ لِرَسُولٍ حَتَّىٰ
يَأْتِيَنَا بِقُرْبَانٍ تَأْكُلُهُ ٱلنَّارُ ۗ قُلْ قَدْ جَآءَكُمْ رُسُلٌ مِّن قَبْلِى بِٱلْبَيِّنَٰتِ وَبِٱلَّذِى قُلْتُمْ
فَلِمَ قَتَلْتُمُوهُمْ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ١٨٣ فَإِن كَذَّبُوكَ فَقَدْ كُذِّبَ رُسُلٌ مِّن قَبْلِكَ جَآءُو
بِٱلْبَيِّنَٰتِ وَٱلزُّبُرِ وَٱلْكِتَٰبِ ٱلْمُنِيرِ ١٨٤

**181-184.** አላህ የእነዚያን አላህ ድሃ ነው እኛ ግን ከበርቴዎች ነን ያሉትን ሰዎች ቃል በእርግጥ ሰማ። ያንን ያሉትንና ነብያትን ያለ ህግ መግደላቸውን በእርግጥ እንፅፋለን። የእሳትንም ስቃይ ቅመሱ እንላቸዋለን። ያ፣ ስቃይ እጃችሁ ባሳለፋት ስራና አላህ ለባሮቹ በዳይ ባለመሆኑ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ ይህን ቃል የተናገሩት ለማንኛውም መልዕክተኛ እሳት የምትበላው ቁርባን እስከሚያመጣልን ድረስ በሱ እንዳናምን አላህ ወደ እኛ አዝዟል ያሉ ናቸው። ብዙ መልዕክተኞች ከእኔ በፊት በግልፅ ተዐምራትና በዚያ ባላችሁት

ቁርባን በእርግጥ መጥተውላችኋል። እውነተኞች ከሆናችሁ ታዲያ ለምን ገደላችኋቸው? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢያስተባብሉህ ከአንተ በፊት በግልፅ ተዐምራትን በፅሁፎች በብሩህ መጽሐፍም የመጡ መልዕክተኞችም በእርግጥ በእነርሱ መሰሎች ተስተባብለዋል።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (181) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ አቡበክር ሲዲቅ አንድ ቀን ወደ አይሁዶች መሰብሰቢያ ቦታ ገብተው ፊንሀስ ኢብኑ አዙራ ለተባለው አለቃቸው «አላህን ፍራ ኢስላምን ተቀበል። የነብዩ ነብይነት ከመፅሐፋችሁ ላይ በደንብ ስለተገለፀ እውነት መሆኑን በትክክል ታውቃላችሁ። ይልቁንስ ስለምና ለጌታህ መልካም ብደር አበድር። ጀነትን ይሰጥሃል። ምንዳና ምንዳን ያነባብርልሃል» ሲሉት መለስ አድርጎ አንተ እንደምትለው ከሆነ ጌታችሁ የገንዘብ ብድር ይፈልጋል። የሚበደር ደግሞ ድሃ ነው። ስለዚህ አላህ ደሃ ነው ማለት ነው ሲላቸው አቡበክር ተናድደው አፍንጫውን በቡጢ መቱትና «በጌታዬ ይሁንብኝ በመሀከላችን ያለው ቃል ኪዳን ባልኖረ አንገትህን እቆርጠው ነበር» አሉት። ፊንሀስ ግን ወደ ነብዩ ሄዶ «ሙሐመድ ሆይ ተመልከት ጓደኛህ ያደረገኝን» በማለት ከሰሳቸው። ነብዩም አቡበከርን አስጠርተው «ለምን እንዲህ አደረክ» ሲሏቸው «ፊንሀስ አስቀያሚ ንግግር ስለተናገረ ነው«በማለት መለሱ። ፊንሀስ ግን «አይኔን ግንባር ያድርገው ምንም አልተናገርኩም» በማለቱ የጉዳዩን እውነታ ለማብራራት እና እውነቱ የአቡ በክር እንደነበር ለመግለፅ የወረደ ነው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (183) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ከዕብ ኢብኑ አልአሽረፍ እና ጓዶቹ ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት «አላህ ወደ እናንተ መልዕክተኛ አድርጎ ልኮኛል። መፅሐፍም በእኔ ላይ አውርዷል እያልክ አይደለም እንዴ? አላህ ደግሞ በተውራት ያዘዘን ነገር ቢኖር ማንኛውም ነብይ ነኝ የሚልን ሰው ቁርባን አምጥቶ እሳት እስካልበላው ድረስ እንዳናምን ነውና ይህን ካደረክ እናምንሃለን«በማለታቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ እና ቁርጡቢ)

كُلُّ نَفْسٍ ذَآئِقَةُ ٱلْمَوْتِۗ وَإِنَّمَا تُوَفَّوْنَ أُجُورَكُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِۖ فَمَن زُحْزِحَ عَنِ ٱلنَّارِ وَأُدْخِلَ ٱلْجَنَّةَ فَقَدْ فَازَۗ وَمَا ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَآ إِلَّا مَتَـٰعُ ٱلْغُرُورِ ﴿١٨٥﴾

**185.** ነፍስ ሁሉ ሞትን በእርግጥ ቀማሽ ናት። ምንዳዎቻችሁንም በትክክል የምትሞሉት በትንሳኤ ቀን ብቻ ነው። ከእሳት እንዲርቅ ተደርጎ ገነት እንዲገባ የተደረገ ሰው ሁሉ በእርግጥ ምኞቱን አገኘ። የቅርቢቱ ሕይወት የማታለያ መሳሪያ እንጂ ሌላ አይደለችም።

۞لَتُبْلَوُنَّ فِىٓ أَمْوَٰلِكُمْ وَأَنفُسِكُمْ وَلَتَسْمَعُنَّ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَـٰبَ مِن قَبْلِكُمْ وَمِنَ ٱلَّذِينَ أَشْرَكُوٓا۟ أَذًى كَثِيرًاۚ وَإِن تَصْبِرُوا۟ وَتَتَّقُوا۟ فَإِنَّ ذَٰلِكَ مِنْ عَزْمِ ٱلْأُمُورِ ﴿١٨٦﴾

**186.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በገንዘቦቻችሁና በነፍሶቻችሁ ትፈተናላችሁ። ከእነዚያ ከናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡትና ከእነዚያ በአላህ ከአጋሩት ቡድኖች ብዙ መጥፎ ነገሮችን ትሰማላችሁ። ብትታገሱና ብትጠነቀቁ በጣም ጥሩ ነው። ይህ ተግባር ከታላላቅ ነገሮች አንዱ ነው።

وَإِذۡ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ لَتُبَيِّنُنَّهُۥ لِلنَّاسِ وَلَا تَكۡتُمُونَهُۥ فَنَبَذُوهُ وَرَآءَ
ظُهُورِهِمۡ وَٱشۡتَرَوۡاْ بِهِۦ ثَمَنٗا قَلِيلٗاۖ فَبِئۡسَ مَا يَشۡتَرُونَ ١٨٧ لَا تَحۡسَبَنَّ ٱلَّذِينَ يَفۡرَحُونَ بِمَآ
أَتَواْ وَّيُحِبُّونَ أَن يُحۡمَدُواْ بِمَا لَمۡ يَفۡعَلُواْ فَلَا تَحۡسَبَنَّهُم بِمَفَازَةٖ مِّنَ ٱلۡعَذَابِۖ وَلَهُمۡ عَذَابٌ
أَلِيمٞ ١٨٨ وَلِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ١٨٩

**187-189.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የእነዚያ መፅሐፍን የሰጡትን ለሰዎች በእርግጥ አብራሩት እንጂ አትደብቁት በማለት የያዘባቸውን ቃል ኪዳን (አስታውስ)። እናም በጀርባዎቻቸው በኋላ ወረወሩት። በእርሱም ጥቂትን ዋጋ ገዙበት። የሚገዙትም ነገር ከፋ። እነዚያን በሰሩት ነገር የሚደሰቱና ባልሰሩትም መመስገንን የሚወዱ ሰዎችን ከቅጣት በመዳን ላይ ናቸው ብለህ አታስባቸው። ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለባቸውና። የሰማያትና የምድር ንግስና የአላህ ብቻ ስልጣን ነው። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (188) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አስመሳዮች ነብዩ (ﷺ) ወደ ጦርነት ሲወጡ ወደ ኋላ ይቀሩና ሲመጡ እየማሉ ይቅርታ ከመጠየቃቸውም አልፈው ባልሰሩት መመስገን ይፈልጉ ነበርና ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

إِنَّ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ لَأٓيَٰتٖ لِّأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ١٩٠ ٱلَّذِينَ
يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ قِيَٰمٗا وَقُعُودٗا وَعَلَىٰ جُنُوبِهِمۡ وَيَتَفَكَّرُونَ فِي خَلۡقِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ رَبَّنَا
مَا خَلَقۡتَ هَٰذَا بَٰطِلٗا سُبۡحَٰنَكَ فَقِنَا عَذَابَ ٱلنَّارِ ١٩١ رَبَّنَآ إِنَّكَ مَن تُدۡخِلِ ٱلنَّارَ فَقَدۡ
أَخۡزَيۡتَهُۥۖ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ أَنصَارٖ ١٩٢ رَّبَّنَآ إِنَّنَا سَمِعۡنَا مُنَادِيٗا يُنَادِي لِلۡإِيمَٰنِ أَنۡ ءَامِنُواْ
بِرَبِّكُمۡ فَـَٔامَنَّاۚ رَبَّنَا فَٱغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَا وَكَفِّرۡ عَنَّا سَيِّـَٔاتِنَا وَتَوَفَّنَا مَعَ ٱلۡأَبۡرَارِ ١٩٣ رَبَّنَا
وَءَاتِنَا مَا وَعَدتَّنَا عَلَىٰ رُسُلِكَ وَلَا تُخۡزِنَا يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۗ إِنَّكَ لَا تُخۡلِفُ ٱلۡمِيعَادَ ١٩٤

**190-194.** በሰማያትና በምድር መፈጠር በሌሊትና በቀንም መተካካት ለባለ አእምሮዎች ሁሉ ታላላቅ ምልክቶች አሉ። እነርሱም እነዚያ ቆመው ተቀምጠውም በጎኖቻቸው ተጋድመውም አላህን የሚያወሱ በሰማያትና በምድር አፈጣጠርም የሚያስተነትኑ ጌታችን ሆይ! ይህን በከንቱ አልፈጠርከውም ጥራት ይገባህ። ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን የሚሉ ናቸው።

ጌታችን ሆይ! አንተ እሳት የምታስገባው ሰው ሁሉ በእርግጥ አዋረድከው። ለበደለኞች ምንም ረዳቶች የሏቸውም። ጌታችን ሆይ! እኛ በጌታችሁ እመኑ በማለት ወደ እምነት የሚጠራን ጠሪ ሰማንና ወዲያዉኑ አመንም። ጌታችን ሆይ! ኃጢአቶቻችንንም ለኛ ማርልን ክፉ ስራዎቻችንንም ከኛ አብስልን። ከንፁሆች ሰዎች ጋርም ግደለን። ጌታችን ሆይ! በመልዕክተኞቹ አማካኝነት የሰጠኸንን፤ የገባህልንን የተስፋ ቃል ስጠን። በትንሳኤ ቀንም አታዋርደን። አታሳፍረን። አንተ ቀጠሮን አታፈርስምና (የሚሉ ናቸው።)

فَٱسۡتَجَابَ لَهُمۡ رَبُّهُمۡ أَنِّي لَآ أُضِيعُ عَمَلَ عَٰمِلٖ مِّنكُم مِّن ذَكَرٍ أَوۡ أُنثَىٰۖ بَعۡضُكُم مِّنۢ بَعۡضٖۖ فَٱلَّذِينَ هَاجَرُواْ وَأُخۡرِجُواْ مِن دِيَٰرِهِمۡ وَأُوذُواْ فِي سَبِيلِي وَقَٰتَلُواْ وَقُتِلُواْ لَأُكَفِّرَنَّ عَنۡهُمۡ سَيِّـَٔاتِهِمۡ وَلَأُدۡخِلَنَّهُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ ثَوَابٗا مِّنۡ عِندِ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ عِندَهُۥ حُسۡنُ ٱلثَّوَابِ ١٩٥

**195.** እናም ጌታቸው እኔ ከናንተ ውስጥ የወንድም ሆነ የሴትን የሰሪን መልካም ስራ ወረታን አላጠፋም። ከፊላችሁ የከፊሉ አካል ነው በማለት ልመናቸውን ተቀበላቸው። እነዚያ ለዲን ሲሉ የተሰደዱ ከአገሮቻቸውም በግፍ የተባረሩ በመንገዴም (ሁከት የደረሰባቸው) የተጠቁ፤ የተጋደሉ እና የተገደሉም ክፉ ስራዎቻቸውን አብስላቸዋለሁ። በስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈስባቸውን ገነቶች አስገባቸዋለሁ። እነርሱም ከአላህ ዘንድ የሆነን ከፍተኛ ምንዳ ይመነዳሉ። አላህ እርሱ ዘንድ መልካም (ጀነት) ምንዳ አለና።

لَا يَغُرَّنَّكَ تَقَلُّبُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي ٱلۡبِلَٰدِ ١٩٦ مَتَٰعٞ قَلِيلٞ ثُمَّ مَأۡوَىٰهُمۡ جَهَنَّمُۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمِهَادُ ١٩٧ لَٰكِنِ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوۡاْ رَبَّهُمۡ لَهُمۡ جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَا نُزُلٗا مِّنۡ عِندِ ٱللَّهِۗ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ خَيۡرٞ لِّلۡأَبۡرَارِ ١٩٨

**196-198.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የእነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች በየአገሮች መንፈላሰስ አያታልህ (አይግረምህ)። አነስተኛ ጥቅም ነውና። ከዚያ መኖሪያቸው ገሀነም ናት። ገሀነም ደግሞ ማረፊያነቷ ምን ትከፋ። እነዚያ ጌታቸውን የፈሩ ሰዎች ግን ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች በውስጧ ዘወታሪዎች ሲሆኑ አላህ ዘንድ የተሰጡ መስተንግዶዎች አሏቸው። አላህም ዘንድ ያለው ምንዳ ለበጎ ሰሪዎች ሁሉ በላጭ ነው።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (196) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከዕብ ኢብኑ አልአሽረፍ የተባለው አይሁድ ገጣሚ ነብዩን ይሳደብ ስለነበር እና የመካ ከሐዲያንም በዚሁ ላይ የሚያጠናክር ነበር። ነብዩ ወደ መዲና ሲሰደዱ የመዲና ሰዎች ግማሹቹ ሙስሊሞች ሌሎቹም አይሁድና አጋሪዎች ስለ ነበሩ በነብዩ አስማምተው መኖር ቢፈልጉም አይሁዶችና አጋሪዎች በተለያየ መልኩ ነብዩንም ሆነ ሶሀቦቻቸውን ሲያሰቃዩዋቸው ትግስት እንዲያደርጉ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ቁርጡቢ)

وَإِنَّ مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ لَمَن يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْكُمْ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِمْ خَٰشِعِينَ لِلَّهِ لَا يَشْتَرُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ ثَمَنًا قَلِيلًا ۗ أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ أَجْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ سَرِيعُ ٱلْحِسَابِ ﴿١٩٩﴾
يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱصْبِرُوا۟ وَصَابِرُوا۟ وَرَابِطُوا۟ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٢٠٠﴾

**199-200.** ከመጽሐፍ ባለቤቶች መካከል አላህን ፈሪዎችና በአላህ አንቀፆችም ጥቂትን ዋጋ የማይለውጡ ሲሆኑ በአላህና በዚያ ወደ እናንተ በተወረደው ቁርኣን በዚያም ወደ እነርሱ በተወረዱት ልዩ ልዩ መፅሐፍት የሚያምኑ ሰዎች አሉ። እነዚያ ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ ተገቢው ምንዳቸው አለላቸው አላህ ምርመራው ፈጣን ነው። እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከእሳት ቅጣት ትድኑ ዘንድ ታገሱ። ተበራቱም። በጦር ኬላ ላይ ሆናችሁ ተሰለፉ አላህንም በትክክል ፍሩ።

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (199) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ነጃሺ በሞተ ጊዜ የርቀት ሶላት (ሶላት አል -ጋኢብ) ሲሰግዱበት አስመሳዮች «ይኸውላችሁ አይቶት በማያውቅና ሃይማኖቱን በማይከተል ጠብደል የሐበሻ ከሃዲ ላይ ይሰግዳል» ሲሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፣ ሱዩጢ እና ኢብኑ-አልጀውዚ)

ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ (200) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩ ጊዜ የሚጠበቅ ኬላ ያልነበረ ቢሆንም አንድን ሶላት ከሰገዱ በኋላ ሌላን ሶላት ለመስገድ ያደርጉት የነበረው በመስጊድ መጠባበቅ እንደ ኬላ ጥበቃ በመቆጠሩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሓኪም እና ዋሒዲ)

**ከዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (181-200) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአይሁድን ክህደትና ከነብያት ጋር የነበራቸውን ጥሩና መጥፎ ግንኙነት፣
2. ነብያትን መግደል እጅግ አስከፊ ቅጣት ውስጥ የሚከት ከባድ ወንጀል መሆኑን፣
3. አይሁድ እሳት የሚበላውን ቁርባን ያላመጣን ነብይ እንዳንቀበል አላህ ከልክሎናል ማለታቸው ውሸት መሆኑን፣
4. ዱንያ የስራ እንጂ የምንዳ ሀገር አለመሆኗን፡
5. የመፅሐፍ ባለቤቶች ምሁራን ላይ አላህ ቃል ኪዳን መያዙን፣
6. ሙስሊም ባልሰራው ነገር ላይ ምስጋና እንዲሰጠው መፈለግ እንደሌለበት፣
7. አላህ የሁሉም ነገር ንጉሰ. ነገስት መሆኑን፣
8. በሰማይና በምድር አፈጣጠር ላይ በመመራመር የአላህን ታላቅነት ማስተንተን ተገቢ መሆኑን፣

9. በመኝታ፤ በመቆም፤ በመቀመጥም ሆነ በመንቀሳቀስ ጊዜ አላህን ማውሳት የጥሩ አማኝነት ምልክት መሆኑን፤
10. አላህን ከእሳት ቅጣት እንዲጠብቀን መለመን ተገቢ መሆኑን፤
11. በመልካም ስራ ወደ አላህ መማለድ ተፈላጊ መሆኑን፤
12. ለሃይማኖት ለኢስላም ብሎ ስደት መውጣትና ጂሃድ ማድረግ ያለው ምንዳ ከፍተኛ መሆኑን፤
13. ሴትና ወንድ በአላህ ዘንድ በሰሩት መልካም ስራ እኩል ምንዳ እንደሚያገኙ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የዒምራን ቤተሰቦች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (4)
# የሴቶች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አን-ኒሳእ)

سُورَةُ النِّسَاءِ

**የወረደው በመዲና ነው። የምዕራፉ አናቅፅ ብዛት (176) መቶ ሰባ ስድስት ናቸው።**

### የሱረቱ አን-ኒሳእ መግቢያ

ምእራፉ ብዙ ቁም ነገሮችን ያጠቃለለ ነው። በተለይም:-ስያሜውን ያገኘበትን የሴቶችን ጉዳይ በሰፊው ይዳስሳል።

-በሰዎች አፈጣጠር ሂደት የሴቶች ሚና ከወንዶች ያላነሰ መሆኑን፤ የቲም ሴቶችን በይበልጥ መንከባከብ ተገቢ መሆኑን፤ የጋብቻን አስፈላጊነት፤ ከአንዲት ሴት በላይ ማግባት መፈቀዱም ከማህበራዊ ችግሮች ማቃለያ ሂደቶች አንዱ መሆኑን፤ እርሱም የሚፈቀደው መስፈርቶቹን ላሟሉ ሰዎች ብቻ እንጂ ለማንም የሚፈቀድ እንዳልሆነ፤ ባል በሚስት፤ ሚስት በባል ላይ ያላቸዉን መብቶችና በመካከላቸው ለሚፈጠሩ አለመግባባቶች መፍተሄዎችን መጠቆም እና እርስ በእርስ መደጋገፍና መተባበር፤ ፍትሃዊነትና ታማኝነት የማህበራዊ ዋልታዎች እንደሆኑ ያስተምራል።

ምእራፉ የሚጠቃለለው ክርስቲያኖች ስለ ነብዩ ዒሳ ያላቸው እምነት ስህተት እንደሆነ በግልፅ በማስረዳት ነው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمُ ٱلَّذِي خَلَقَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ وَخَلَقَ مِنۡهَا زَوۡجَهَا
وَبَثَّ مِنۡهُمَا رِجَالٗا كَثِيرٗا وَنِسَآءٗۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِي تَسَآءَلُونَ بِهِۦ وَٱلۡأَرۡحَامَۚ
إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَيۡكُمۡ رَقِيبٗا ١

**1.** እናንተ ሰዎች ሆይ፣ ያንን ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁን፣ ከእርሷም መቀናጆዋን (ሀዋን) የፈጠረውንና ከሁለቱም ብዙ ወንዶችንና ሴቶችን የበተነውን ጌታችሁን (አላህን) ፍሩ። ያንንም በርሱ የምትጠያየቁበትን አላህን (ከሚያስቆጡ) ተግባራትና ዝምድናዎችን (ከመቁረጥ) ተጠንቀቁ። አላህ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ ነውና።

وَءَاتُواْ ٱلۡيَتَٰمَىٰٓ أَمۡوَٰلَهُمۡۖ وَلَا تَتَبَدَّلُواْ ٱلۡخَبِيثَ بِٱلطَّيِّبِۖ وَلَا تَأۡكُلُوٓاْ أَمۡوَٰلَهُمۡ إِلَىٰٓ أَمۡوَٰلِكُمۡۚ
إِنَّهُۥ كَانَ حُوبٗا كَبِيرٗا ٢ وَإِنۡ خِفۡتُمۡ أَلَّا تُقۡسِطُواْ فِي ٱلۡيَتَٰمَىٰ فَٱنكِحُواْ مَا طَابَ لَكُم
مِّنَ ٱلنِّسَآءِ مَثۡنَىٰ وَثُلَٰثَ وَرُبَٰعَۖ فَإِنۡ خِفۡتُمۡ أَلَّا تَعۡدِلُواْ فَوَٰحِدَةً أَوۡ مَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُمۡۚ
ذَٰلِكَ أَدۡنَىٰٓ أَلَّا تَعُولُواْ ٣

**2-3.** ለየቲሞች ገንዘቦቻቸውን ስጡ። ከመህከሉም መጥፎውንም በመልካሙ አትለውጡ። ገንዘቦቻቸውን ወደ ገንዘቦቻችሁ (በመቀላቀል) አትብሉ። እርሱ ታላቅ ኃጢአት ነውና። (እናንተ ሙስሊም ወንዶች ሆይ) በናንተ ስር ያሉት ሴት የቲሞችን በማግባታችሁ አለማስተካከላችሁን ብትፈሩ (የቲም ካልሆኑ ሴቶች መካከል) ለእናንተ የመረጣችሁትን (ደስ ያላችሁን) ሁለት ሁለት ሶስት ሶስትና አራት አራት አግቡ። በሚስቶች መካከል አለማስተካከላችሁን ብትፈሩ ግን አንዲትን ሴት ብቻ ወይም ንብረታችሁ የሆኑትን አገልጋይ ሴት ባሪያዎችን ብቻ (በሚስትነት) ያዙ። ይህም ሴትን ልጅ እንዳትበድሉ በጣም የቀረበ ተግባር ነው።

ከሴቶች ምዕራፍ (2) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ የሐብታም ወንድሙን ልጅ የሚያሳድግ ሰው ልጁ ለአቅመ አዳም ሲደርስና ገንዘቡን ሲጠይቀው እንቢ በማለቱ ጉዳያቸው ወደ ነብዩ (ﷺ) እንዲቀርብ በተደረገ ጊዜ እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። አጎትየውም እነዚህን አናቅፅ ሲሰማ አላህን እና መልዕክተኛውን ታዝዘናል። ከታላቅ ወንጀል አላህ ይጠብቀን። በማለት ተፀፅቶ ለልጁ

ንብረቱን አስረከበው። ነብዩ (ﷺ) «የግል ስሜቱን ያሸነፈ ልክ እንደዚህ ያስተካከለ ሰው ቦታውን (ጀነትን) ያገኛል» አሉ። ልጁም ገንዘቡ ሲደርሰው ለዲን አወጣው። በዚህም ሰዐት ነብዩ (ﷺ) «ምንዳው ተረጋገጠ። ወንጀሉም ቀረ» አሉ። ሶሃቦች «ምንዳው የተባለውን አወቅነው ወንጀሉ የትኛው ነው»ብለው ሲጠይቋቸው«ምንዳው ለልጁ ሲሆን ወንጀሉ ግን ለአባቱ ነው። ምክንያቱም በአላህ የሚያጋራ ነበርና» አሉ። (ዋሒዲ እና ቁርጡቢ)

ከሴቶች ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የቲሞችን ልጆችን የሚያስተዳድሩና የሚያሳድጉ ሰዎች የቲምነታቸውን ምክንያት አድርገው በጋብቻ ወቅት ሲድሯቸው ከጓደኞቻቸው በታች በሆነ መህር እንዳይጫኗቸው ትንሽ መህር ብቻ እንዳይቀበሉላቸው ለማስተማር የወረደ አንቀፅ ነው። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَءَاتُواْ ٱلنِّسَآءَ صَدُقَٰتِهِنَّ نِحۡلَةٗۚ فَإِن طِبۡنَ لَكُمۡ عَن شَيۡءٖ مِّنۡهُ نَفۡسٗا فَكُلُوهُ هَنِيٓـٔٗا
مَّرِيٓـٔٗا ٤ وَلَا تُؤۡتُواْ ٱلسُّفَهَآءَ أَمۡوَٰلَكُمُ ٱلَّتِي جَعَلَ ٱللَّهُ لَكُمۡ قِيَٰمٗا وَٱرۡزُقُوهُمۡ فِيهَا
وَٱكۡسُوهُمۡ وَقُولُواْ لَهُمۡ قَوۡلٗا مَّعۡرُوفٗا ٥

**4-5.** ለሴቶች መህሮቻቸውን ደስተኞች ሆናችሁ ስጧቸው። ለእናንተ ከእርሱ የተወሰነን ነገር ራሳቸው ቢለግሱላችሁ ግን መልካምና የተመሰገነ ሲሆኑ ብሉት። (ተጠቀሙበት)። (ኃላፊዎች ሆይ!) ያን አላህ ለእናንተ መተዳደሪያ (መጠቃቀሚያ) ያደረገውን* ገንዘባችሁን የያዛችሁላቸውን ለቂሎች (ለአዕምሮ ደካሞች) አትስጧቸው። ከእርሷም መግቧቸው። ከእርሷም አልብሷቸውም። ለእነርሱም መልካምን ንግግር ተናገሯቸው።

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ለወላጆች ቅን አለመሆንን፤ ሴት ልጆችን ከነሕይወታቸው መቅበርን፤ የሌሎቹን መብት አለመስጠት ዘካን አለመስጠትንና ሰዎችን መለመንን ክልክል አድርጎባችኋል። እንዲሁም አላስፈላጊ ጥቅም አልባ ንግሮችን በሰዎች ላይ መናገርን፤ ጥያቄ ማብዛትንና ገንዘብኑ ካለአግባብ ማጥፋትን የተጠላ አድርጓችኋል»

4ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አባት ልጁን ሲድር የሚሰጣትን መህር ሙሉ በሙሉ ይወስድባት ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَٱبۡتَلُواْ ٱلۡيَتَٰمَىٰ حَتَّىٰٓ إِذَا بَلَغُواْ ٱلنِّكَاحَ فَإِنۡ ءَانَسۡتُم مِّنۡهُمۡ رُشۡدٗا فَٱدۡفَعُوٓاْ إِلَيۡهِمۡ أَمۡوَٰلَهُمۡۖ
وَلَا تَأۡكُلُوهَآ إِسۡرَافٗا وَبِدَارًا أَن يَكۡبَرُواْۚ وَمَن كَانَ غَنِيّٗا فَلۡيَسۡتَعۡفِفۡۖ وَمَن كَانَ فَقِيرٗا
فَلۡيَأۡكُلۡ بِٱلۡمَعۡرُوفِۚ فَإِذَا دَفَعۡتُمۡ إِلَيۡهِمۡ أَمۡوَٰلَهُمۡ فَأَشۡهِدُواْ عَلَيۡهِمۡۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ حَسِيبٗا ٦

**6.** (ሙስሊሞች ሆይ!) የቲሞች ለጋብቻ እስከደረሱ ድረስ ፈትኗቸው። ከእነርሱ መካከልም ብልህነትን ብታውቁ ገንዘቦቻቸውን ስጧቸው። ማደጋቸውን በመሽቀዳደምና በማባከን ገንዘቦቻቸውን አትብሉባቸው።

(ከአሳዳጊዎች መካከል) ሀብታም የሆነ ሰው ከገንዘቦቻቸው (ቅንጣት ያህል እንኳን ከመቅረብ) ይከልከል። ደሃ የሆነ ሰውም ቢሆን ለድካሙ ብቻ በአግባቡ ይብላ። ገንዘቦቻቸውን ወደ ነርሱ በሰጣችሁም ጊዜ በእነርሱ ላይ አስመስክሩ። ተጠባባቂነትም አላህ በቂ ነው።

ከሴቶች ምዕራፉ ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሳቢት ቢን ረፋአህ የተባለ ሰው ህፃን ልጁን ጥሎ ሲሞት አጎቱ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ «ወንድሜ ህፃን ልጁን ጥሎ ሞቷል። ከእርሱ ገንዘብ ለእኔ ምንድነው የሚፈቀድልኝ? ለእሱስ ገንዘቡን መመለስ ያለብኝ መቼ ነው?» ብሎ ሲጠይቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

**ከሴቶች ከአንቀፅ (1-6) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህን መፍራት ከኢስላም ድንጋጌዎች ዋነኛው መሆኑን፤
2. በኢስላም ዝምድናን መቀጠል ግዴታ ስለመሆኑ፤
3. በኢስላም ዝምድናን መቁረጥ የተከለከለ ስለመሆኑ፤
4. ወንድማማችነትን በማጠናከር እንዳይላላ መጠበቅ ከኢስላም ግዴታዎች አንዱ መሆኑን፤
5. የሰው ልጅ ምንጭ አንድ ስለመሆኑ፤
6. ሴት ልጅ በቅድመ ኢስላም የእኩይ ነገሮች ሁሉ ምንጭ ተደርጋ ትቆጠር እንደነበረ፤
7. የሰው ልጅ አንድ ቤተሰብ መሆኑን፤
8. በተከለከለ መንገድ የሚገኝ ገንዘብ በሙሉ ቆሻሻ መሆኑንና በተፈቀደ መንገድ የሚገኝ ደግሞ በሙሉ ንፁህ መሆኑን፤
9. የቲሞችን የሚያሳድግ ተወካይ የእነርሱን ሃብት ወስዶ በመጥፎ ገንዘብ መቀየሩም ሆነ ከራሱ ገንዘዘብ ጋር አደባልቆ መስራት እንደማይፈቀድ፤
10. ሙስሊም ወንዶች አራት ሚስቶች ማግባት የሚፈቀድላቸው መሆኑን፤
11. በጋብቻ ወቅት ወንዱ ለሴቷ የጥሎሽ ገንዘብ መስጠቱ ግዴታ መሆኑንና ሴቷ ፈቃደኛ ካልሆነች በስተቀር የስጦታ ገንዘቧን መብላት የተከለከለ መሆኑን፤
12. ከጋብቻ በፊት መምረጥ እንዳለና ለዚህም ሲባል ማየት የተከለከሉትን ቦታዎች ፊትን እጅን የመሳሰሉትን አካሎቿን እስከ ማየት ድረስ እንደተፈቀደ፤
13. በኢስላም ራሳቸውን በትክክል ማስተዳደር በማይችሉ ሰዎች ላይ ማዕቀብ መጣል ተገቢ መሆኑን፤
14. የአዕምሮ በሽተኞችን ሀብት የማስተዳድር ውክልና የተሰጠው ሰው ገንዘባቸውን ለእነርሱ ከመስጠቱ በፊት ምን ያህል ንብረታቸውን በስርዓቱ ማስተዳደር እንደሚችሉ መፈተን እንዳለበት።
15. የቲሞች አድገው ለአቅመ አዳም ሲደርሱ አሳዳጊያቸው ያላቸውን ገንዘብና ንብረት ሲያስረክባቸው ማስመስከር ተገቢ እንደሆነ፤
16. የየቲም አሳዳጊ ተወካይ ግለሰብ ሀብታም ከሆነ ከእነርሱ ገንዘብ መብላት የተከለከለ መሆኑና ድሃ ከሆነ ግን በብድር መልክ ወስዶ መመለስ እንሚችል፤
17. ስለ ቀለብና ስለ ልብስ ጉዳይ ሀላፊያቸው የሚያቀርበው ተቀባይነት እንዳለው እንማራለን።

لِّلرِّجَالِ نَصِيبٞ مِّمَّا تَرَكَ ٱلۡوَٰلِدَانِ وَٱلۡأَقۡرَبُونَ وَلِلنِّسَآءِ نَصِيبٞ مِّمَّا تَرَكَ ٱلۡوَٰلِدَانِ
وَٱلۡأَقۡرَبُونَ مِمَّا قَلَّ مِنۡهُ أَوۡ كَثُرَۚ نَصِيبٗا مَّفۡرُوضٗا ٧ وَإِذَا حَضَرَ ٱلۡقِسۡمَةَ أُوْلُواْ ٱلۡقُرۡبَىٰ
وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينُ فَٱرۡزُقُوهُم مِّنۡهُ وَقُولُواْ لَهُمۡ قَوۡلٗا مَّعۡرُوفٗا ٨

**7-8.** ለወንዶች ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች (ሲሞቱ) ከተውት (ጥሪት ገንዘብ የውርስ) ድርሻ አላቸው። ለሴቶችም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ከእርሱ ይነስም ይብዛም (የውርስ) ድርሻ አላቸው። ለሁሉም የተወሰነ ድርሻ (ተደንግጓል)። የውርስ ክፍፍልን (ወራሽ ያልሆኑ) የዝምድና ባለቤቶች፤ የቲሞችና ሚስኪኖች በተገኙበት ጊዜ ከእርሱ ለግሱላቸው። መልካምንም ንግግር ተናገሯቸው።

وَلۡيَخۡشَ ٱلَّذِينَ لَوۡ تَرَكُواْ مِنۡ خَلۡفِهِمۡ ذُرِّيَّةٗ ضِعَٰفًا خَافُواْ عَلَيۡهِمۡ فَلۡيَتَّقُواْ ٱللَّهَ
وَلۡيَقُولُواْ قَوۡلٗا سَدِيدًا ٩ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَأۡكُلُونَ أَمۡوَٰلَ ٱلۡيَتَٰمَىٰ ظُلۡمًا
إِنَّمَا يَأۡكُلُونَ فِي بُطُونِهِمۡ نَارٗاۖ وَسَيَصۡلَوۡنَ سَعِيرٗا ١٠

**9-10.** እነዚያ ከኋላቸው ደካሞችን ዝርያዎች ቢተው ኖሮ በእነርሱ ላይ ምን ይደርስባቸው ይሆን ብለው የሚፈሩ (የሚሰጉ) ሰዎች ሁሉ (በየቲሞችም ላይ) ይህንኑ ይፍሩ (ይጠንቀቁ)። አላህንም ይፍሩ። ትክክለኛንም ቃል ይናገሩ። እነዚያ የየቲሞችን ገንዘቦች በመበደል (በግፍ) የሚበሉት ሰዎች ሁሉ በሆዶቻቸው ውስጥ የሚበሉት እሳትን ብቻ ነው። እሳትንም በእርግጥ ይገባሉ።

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (8-10) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አንድ መርድ ቢን ዘይድ የተባለ ሰው የወንድሙን የቲም (አባት የሌለው) አሳዳጊ ነበረና ይህ ግለሰብ የየቲሙን ገንዘብ ስላጠፋውና ስለተጠቀመበት እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። (ዋሒዲ፤ ቁርጡቢ እና ኢብኑል-ጀውዚ)

يُوصِيكُمُ ٱللَّهُ فِيٓ أَوۡلَٰدِكُمۡۖ لِلذَّكَرِ مِثۡلُ حَظِّ ٱلۡأُنثَيَيۡنِۚ فَإِن كُنَّ نِسَآءٗ فَوۡقَ ٱثۡنَتَيۡنِ فَلَهُنَّ
ثُلُثَا مَا تَرَكَۖ وَإِن كَانَتۡ وَٰحِدَةٗ فَلَهَا ٱلنِّصۡفُۚ وَلِأَبَوَيۡهِ لِكُلِّ وَٰحِدٖ مِّنۡهُمَا ٱلسُّدُسُ مِمَّا
تَرَكَ إِن كَانَ لَهُۥ وَلَدٞۚ فَإِن لَّمۡ يَكُن لَّهُۥ وَلَدٞ وَوَرِثَهُۥٓ أَبَوَاهُ فَلِأُمِّهِ ٱلثُّلُثُۚ فَإِن كَانَ لَهُۥٓ إِخۡوَةٞ
فَلِأُمِّهِ ٱلسُّدُسُۚ مِنۢ بَعۡدِ وَصِيَّةٖ يُوصِي بِهَآ أَوۡ دَيۡنٍۗ ءَابَآؤُكُمۡ وَأَبۡنَآؤُكُمۡ لَا تَدۡرُونَ أَيُّهُمۡ
أَقۡرَبُ لَكُمۡ نَفۡعٗاۚ فَرِيضَةٗ مِّنَ ٱللَّهِۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمٗا ١١

**11.** (ሰዎች ሆይ) አላህ በልጆቻችሁ ውርስ በሚከተለው መልክ ያዛችኋል። ለወንዱ የሁለት ሴቶች ድርሻ ያህል አለው። (ሁለት ወይም) ከሁለት በላይ የሆኑ ሴቶች ልጆች ብቻ ወራሽ ቢሆኑ ለእነርሱ (ሟቹ) ከተወው (ሀብት) ከሶስት ሁለት እጁ ያገኛሉ (አላቸው)። አንዷት ሴት ወራሽ ብትሆን ደግሞ ለእርሷ የሀብቱ ግማሽ አላት። ለሟቹ ለአባቱና ለእናቱም ለእርሱ ልጅ እንዳለው ከሁለቱ ለእያንዳንዱ ከስድስት አንድ አላቸው። ለእርሱ ልጅ ባይኖረውና ወላጆቹ ብቻ ቢወርሱት ለእናቱ ሲሶ አላት። ለእርሱም ወንድሞችና እህቶች ቢኖሩት ለእናቱ ከስድስት አንድ አላት። (ይህም የውርስ ህግ የተባለው) የሚከፋፈለው ከተናዘዘው ኑዛዜ ወይም ከእዳው ክፍያ በኋላ ነው። አባቶቻችሁና ልጆቻችሁ ለእናንተ በመጥቀም ማንኛቸው ይበልጥ ቅርብ እንደሆኑ አታውቁም። ይህም ከአላህ የተደነገገ ነው። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነዉና።

*ከሴቶች ምዕራፉ* **(11)** *ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ከአንዳንድ የተፍሲር ምሁራን እንደተዘገበው የሰዕድ ብን አረቢዕ ሴት ልጆች ታሪክ በአጭሩ እንዲህ ነበር። እናታቸው ሁለቱን ሴት ልጆች ይዛ መጥታ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኒህ የሰዕድ ልጆች ናቸው። አጎታቸው የአባታቸውን ገንዘብ ሙሉ በሙሉ ወሰደው። ያለ ገንዘብ ማግባት አይችሉም። ስትል ነብዩ አላህ መፍትሄ ይሰጣል በማለታቸው ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ ጃቢር ቢን አብደላህ ታሞ በነበረበት ወቅት ነብዩን እና አቡበክር ሊጎበኙት ሲሄዱ እራሱን አንስቶ አገኙት። ከዚያም ነብዩ ውሃ አጠጡትና ውዱእ አስደርገው ሲያፈሱበት ትንሽ ተሻለው። ከዚያም የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ገንዘቤን ምን ላድርገው በማለት ስለጠየቃቸው ነው የወረደው ተብሏል።*

۞ وَلَكُمْ نِصْفُ مَا تَرَكَ أَزْوَٰجُكُمْ إِن لَّمْ يَكُن لَّهُنَّ وَلَدٌ ۚ فَإِن كَانَ لَهُنَّ وَلَدٌ فَلَكُمُ
ٱلرُّبُعُ مِمَّا تَرَكْنَ ۚ مِنۢ بَعْدِ وَصِيَّةٍ يُوصِينَ بِهَآ أَوْ دَيْنٍ ۚ وَلَهُنَّ ٱلرُّبُعُ مِمَّا تَرَكْتُمْ إِن لَّمْ يَكُن
لَّكُمْ وَلَدٌ ۚ فَإِن كَانَ لَكُمْ وَلَدٌ فَلَهُنَّ ٱلثُّمُنُ مِمَّا تَرَكْتُم ۚ مِّنۢ بَعْدِ وَصِيَّةٍ تُوصُونَ بِهَآ أَوْ
دَيْنٍ ۗ وَإِن كَانَ رَجُلٌ يُورَثُ كَلَٰلَةً أَوِ ٱمْرَأَةٌ وَلَهُۥٓ أَخٌ أَوْ أُخْتٌ فَلِكُلِّ وَٰحِدٍ مِّنْهُمَا ٱلسُّدُسُ ۚ
فَإِن كَانُوٓا۟ أَكْثَرَ مِن ذَٰلِكَ فَهُمْ شُرَكَآءُ فِى ٱلثُّلُثِ ۚ مِنۢ بَعْدِ وَصِيَّةٍ يُوصَىٰ بِهَآ أَوْ دَيْنٍ غَيْرَ
مُضَآرٍّ ۚ وَصِيَّةً مِّنَ ٱللَّهِ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَلِيمٌ ﴿١٢﴾

**12.** (ወንዶች ሆይ!) ለእናንተም ሚስቶቻችሁ ሲሞቱ ከተውት ንብረት ለእነርሱ ልጅ ካልኖራቸው ግማሹ አላችሁ። ለእነርሱም ልጅ ቢኖራቸው ከተውት ሀብት ከአራት አንድ አላችሁ። (ይህም) በእርሷ ከሚናዘዙባት ኑዛዜ ወይም ከእዳ ክፍያ በኋላ ነው። ለእናንተም ልጅ ባይኖራችሁ ከተዋችሁት ንብረት

ለእነርሱ (ለሚስቶች) ከስምንት አንድ አላቸው። (ይህም) ከምትናዘዙበት ኑዛዜ ወይም ከእዳ ክፍያ በኋላ ነው። ወላጆችም ልጅም የሌለውና በጎን ወራሾች የሚወርሱት ወንድ ወይም ሴት ቢገኝ ለእነርሱም (ለሟቹ) ከእናቱ በኩል ብቻ የሆኑ ወንድም ወይም እህት ቢኖሩት ከሁለቱ ለእያንደንዳቸው ከስድስት አንድ አላቸው። ከአንድ የበዙ ቢሆን በሲሶ ላይ ተጋሪዎች ናቸው። ይህም ወራሾቹን የማይጎዳ ሆኖ ከእርሷ ከሚናዘዙባት ኑዛዜ ወይም ከእዳ በኋላ ነው። ከአላህም የሆነን ኑዛዜ ያዛችኋል። አላህ አዋቂና ቻይ ነውና።

تِلْكَ حُدُودُ ٱللَّهِ ۚ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ يُدْخِلْهُ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَا ۚ وَذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴿١٣﴾ وَمَن يَعْصِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَيَتَعَدَّ حُدُودَهُۥ يُدْخِلْهُ نَارًا خَٰلِدًا فِيهَا وَلَهُۥ عَذَابٌ مُّهِينٌ ﴿١٤﴾

**13-14.** እነዚህ የአላህ ውሳኔዎች ናቸው። አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዙ ሰዎች ሁሉ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ ያስገባቸዋል። ይህም ትልቅ እድል ነው። በአላህንና መልዕክተኛው ላይ የሚያምፅ የማይታዘዝና ወሰኖችን የሚተላለፍ ሰው ሁሉ በውስጧ ዘውታሪ ሲሆን ወደ ገሀነም እሳት ያስገባዋል። ለእርሱም አዋራጅ ቅጣት አለበት።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (7-14) ከምናገናቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. በኢስላም የውርስ አከፋፈል ራሱን የቻለ ህግ ያለው መሆኑን፤
2. በኢስላም የሟች ሀብት ለወራሾች ሲከፋፈል ከተቻለ በቅርብ ለሚገኙ የቲሞችና ድሆች ዳረጎት መስጠት ካልተቻለ በጥሩ ቃል ማሰናበት ተገቢ መሆኑን፤
3. በፀና ታሞ አልጋ ላይ ለዋለ ሰው ምክር መለገሱ የግድ መሆኑንና፤ በተለይ በኑዛዜ በኩል ጥንቃቄ የተሞላበት ኑዛዜ እንዲያደርግ ማስታወስ እንደሚገባ፤
4. በመሞቱ ምክንያት ልጆቹ ይጎዱብኛል ብሎ የሚያስብ ሰው ልክ ለልጆቹ እንደተጨነቀ ሁሉ ለሌሎች ሰዎች ልጆችም ሊያሳስቡት እንደሚገባ፤
5. የሚያጓጓ ነገር የቀረበለት ሰው ላቀረበለት ሰው በጥቂቱም ቢሆን ከዚያ ነገር ማጉረስ እንዳለበት፤
6. ውርስን እንዴትና ለማን እንደሚከፋፈል አላህ ራሱ ድንጋጌውን እንዳወጣና በህግ መልክ ቁርአን ላይ እንዳሰፈረው፤
7. በኢስላም የሟች እህትና ወንድም ከሟቹ ሀብት ምን ያህል መጠን እንደሚደርሳቸው፤
8. በኢስላም የሟች ወራሾችን ለመጉዳት በማሰብ ሟች የሚናዘዘው ኑዛዜ አሊያም ብድር ተቀባይነት እንደሌለው፤
9. በኢስላም የአላህን ህግ በመተላለፍ የሚፈፀሙ ህገ ወጥነቶች የሚያስከትሉትን አደገኛ መዘዝ፤
10. አላህንና ነብዩን መታዘዙ ተድላና ደስታን እንደሚያስገኝ እነርሱን ማመፁ ደግሞ ሀዘንና ስቃ እንደሚያተርፍ እንገነዘባለን፤

وَٱلَّتِي يَأۡتِينَ ٱلۡفَٰحِشَةَ مِن نِّسَآئِكُمۡ فَٱسۡتَشۡهِدُواْ عَلَيۡهِنَّ أَرۡبَعَةٗ مِّنكُمۡۖ فَإِن شَهِدُواْ
فَأَمۡسِكُوهُنَّ فِي ٱلۡبُيُوتِ حَتَّىٰ يَتَوَفَّىٰهُنَّ ٱلۡمَوۡتُ أَوۡ يَجۡعَلَ ٱللَّهُ لَهُنَّ سَبِيلٗا ﴿١٥﴾

**15.** እነዚያ ከሴቶቻችሁ መካከል ዝሙትን የሚሰሩ በእነርሱ ላይ ከናንተ የሆነን አራት ታማኝ ወንዶችን አስመስክሩባቸው። ከመሰከሩም ሞት እስከሚደርስባቸው ወይም አላህ ለእነርሱ ሌላ መንገድን እስከሚያደርግ ድረስ በቤቶች ውስጥ ያዟቸው*1።*2

*1 ጠብቋቸው ወይም አስቀምጧቸው።

*2 በብርሃኑ ምዕራፍ (2) ኛው አንቀፅ ላይ በተደነገገው ከእስር ሌላ ህግ ተደንግጎላቸዋል።

وَٱلَّذَانِ يَأۡتِيَٰنِهَا مِنكُمۡ فَـَٔاذُوهُمَاۖ فَإِن تَابَا وَأَصۡلَحَا فَأَعۡرِضُواْ عَنۡهُمَآۗ
إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ تَوَّابٗا رَّحِيمًا ﴿١٦﴾

**16.** እነዚያ ከናንተ ውስጥ ዝሙትን የሚሰሩትን አሰቃይዋቸው (በሚገባ ቅጧቸው)። ቢፀፀቱና ስራቸውን ቢያሳምሩ ግን እነርሱን (ተዋቸው) አታሰቃዩዋቸው። አላህ ፀፀትን ተቀባይና አዛኝ ነውና።

إِنَّمَا ٱلتَّوۡبَةُ عَلَى ٱللَّهِ لِلَّذِينَ يَعۡمَلُونَ ٱلسُّوٓءَ بِجَهَٰلَةٖ ثُمَّ يَتُوبُونَ مِن قَرِيبٖ فَأُوْلَٰٓئِكَ يَتُوبُ
ٱللَّهُ عَلَيۡهِمۡۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمٗا ﴿١٧﴾ وَلَيۡسَتِ ٱلتَّوۡبَةُ لِلَّذِينَ يَعۡمَلُونَ ٱلسَّيِّـَٔاتِ حَتَّىٰٓ
إِذَا حَضَرَ أَحَدَهُمُ ٱلۡمَوۡتُ قَالَ إِنِّي تُبۡتُ ٱلۡـَٰٔنَ وَلَا ٱلَّذِينَ يَمُوتُونَ وَهُمۡ كُفَّارٌۚ أُوْلَٰٓئِكَ
أَعۡتَدۡنَا لَهُمۡ عَذَابًا أَلِيمٗا ﴿١٨﴾

**17-18.** ፀፀትን መቀበል በአላህ ላይ የሚገባው ለእነዚያ ኃጢአትን በስህተት ለሚሰሩና ከዚያም ወዲያውኑ ለሚፀፀቱ ሰዎች ብቻ ነው። እነዚያንማ አላህ ከእነርሱ ፀፀትን ይቀበላል። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና። ፀፀትን መቀበል ለእነዚያ ኃጢአቶችን ለሚሰሩና ሞት በመጣባቸው ጊዜ አሁን ተፀፀትኩ ለሚሉና ለእነዚያም ከሐዲያን ሆነው ለሚሞቱ አይደለም። ለእነርሱማ አሳማሚን ቅጣት አዘጋጅተናል።

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (11-12) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የሰዕድ ቢን ረቢዕ ባለቤት ሁለት ሴት ልጆችን ይዛ ወደ ነብዩ ዘንድ በመምጣት እነዚህ ሴት ልጆች ከእርስዎ ጋር ለእሁድ ዘመቻ የወጣውና በዚያው ዘመቻ ሸሂድ (ሰማዕት) የሆነው የሰዕድ ልጆች ናቸው። አጎታቸው ምንም ሳያስቀር ገንዘባቸውን ወስዷል። ስለሆነም ገንዘብ ከሌላቸው ትዳር እንኳን መያዝ አይችሉም። በማለት ትናግራለች። ነብዩ (ﷺ) ትንሽ ታገሺ አላህ ውሳኔ ይሰጣል በማለት መለሷት። ከዚያም

አላህ እነዚህን የውርስ ክፍፍል ስርዓት የሚያስተምሩ አናቅፅን አወረደ። ነብዩም (ﷺ) የየቲሞቹን አጎት አስጠርተው ለሁለት ሴት ልጆች የንብረቱን ሁለት እጅ፤ ለእናታቸው ደግሞ አንድ ስምንተኛ ስጥና ሌላውን አንተ ውሰድ በማለት ቁርአናዊ ፍርድ ሰጡ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا يَحِلُّ لَكُمْ أَن تَرِثُواْ ٱلنِّسَآءَ كَرْهًاۖ وَلَا تَعْضُلُوهُنَّ لِتَذْهَبُواْ بِبَعْضِ مَآ ءَاتَيْتُمُوهُنَّ إِلَّآ أَن يَأْتِينَ بِفَٰحِشَةٖ مُّبَيِّنَةٖۚ وَعَاشِرُوهُنَّ بِٱلْمَعْرُوفِۚ فَإِن كَرِهْتُمُوهُنَّ فَعَسَىٰٓ أَن تَكْرَهُواْ شَيْـٔٗا وَيَجْعَلَ ٱللَّهُ فِيهِ خَيْرٗا كَثِيرٗا ﴿١٩﴾

**19.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ሴቶችን ያስገደዳችሁ ሆናችሁ ልትወርሱና ግልፅ የሆነ መጥፎ ስራ ካልሰሩ በስተቀር ከሰጣችኋቸው ከፊሉን ልትወስዱባቸውና ልታጉላሏቸው አይፈቀድላችሁም። በመልካም ተኗኗሯቸው። ብትጠሏቸውም እንኳን ታገሱ። አንድ ነገር ብትጠሉትም አላህ በእርሱ ብዙ ደግ ነገሮችን ሊያደርግላችሁ ይችላልና።

ከሴቶች ምዕራፍ (19) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በጃሂሊያ ዘመን አንድ ወንድ ሲሞት ሚስቱ ያለ ፈቃዷ እንደ ንብረት ለዘመዶቹ በውርስ ትሰጥ ነበር። ከዚህም አልፎ ከሌላ ሚስት የተወለደው ልጅም ሆነ አባቱ ወይም ወንድሞቹና አጎቶቹ በሟች መህርና ስጦታ ብቻ ቢፈልጉ ሊያገቧት ባይፈልጉ ደግሞ ለፈለጉት ሰው ሊድሯት የሚያስችል ባህል ስለነበራቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። ወንድ በሴት ላይ መብት ያለው እስከ ምን ድረስ እንደሆነም ተገልጿል። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ቁርጡቢ)

وَإِنْ أَرَدتُّمُ ٱسْتِبْدَالَ زَوْجٖ مَّكَانَ زَوْجٖ وَءَاتَيْتُمْ إِحْدَىٰهُنَّ قِنطَارٗا فَلَا تَأْخُذُواْ مِنْهُ شَيْـًٔاۚ أَتَأْخُذُونَهُۥ بُهْتَٰنٗا وَإِثْمٗا مُّبِينٗا ﴿٢٠﴾ وَكَيْفَ تَأْخُذُونَهُۥ وَقَدْ أَفْضَىٰ بَعْضُكُمْ إِلَىٰ بَعْضٖ وَأَخَذْنَ مِنكُم مِّيثَٰقًا غَلِيظٗا ﴿٢١﴾

**20-21.** በሚስት ቦታ ሌላ ሚስት ለመለወጥ ብትፈልጉ (ለምትፈታው ሴት ቀደም ሲል) ብዙን ገንዘብ የሰጣችኋት ስትሆን ከእርሷ ምንንም አትውሰዱባት። በመበደልና ግልፅ በሆነ ኃጢአት ትወስዱታላችሁን? ከፊላችሁ ወደ ከፊሉ የደረሰ ሲሆንና ከናንተ ላይም (ሴቶች) የጠበቀ ቃል ኪዳንን የያዙባችሁ ሲሆኑ እንዴት ትወስዱታላችሁ፤

وَلَا تَنكِحُواْ مَا نَكَحَ ءَابَآؤُكُم مِّنَ ٱلنِّسَآءِ إِلَّا مَا قَدْ سَلَفَۚ إِنَّهُۥ كَانَ فَٰحِشَةٗ وَمَقْتٗا وَسَآءَ سَبِيلًا ﴿٢٢﴾ حُرِّمَتْ عَلَيْكُمْ أُمَّهَٰتُكُمْ وَبَنَاتُكُمْ وَأَخَوَٰتُكُمْ وَعَمَّٰتُكُمْ

وَخَٰلَٰتُكُمۡ وَبَنَاتُ ٱلۡأَخِ وَبَنَاتُ ٱلۡأُخۡتِ وَأُمَّهَٰتُكُمُ ٱلَّٰتِيٓ أَرۡضَعۡنَكُمۡ وَأَخَوَٰتُكُم مِّنَ
ٱلرَّضَٰعَةِ وَأُمَّهَٰتُ نِسَآئِكُمۡ وَرَبَٰٓئِبُكُمُ ٱلَّٰتِي فِي حُجُورِكُم مِّن نِّسَآئِكُمُ ٱلَّٰتِي دَخَلۡتُم
بِهِنَّ فَإِن لَّمۡ تَكُونُواْ دَخَلۡتُم بِهِنَّ فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡكُمۡ وَحَلَٰٓئِلُ أَبۡنَآئِكُمُ ٱلَّذِينَ مِنۡ
أَصۡلَٰبِكُمۡ وَأَن تَجۡمَعُواْ بَيۡنَ ٱلۡأُخۡتَيۡنِ إِلَّا مَا قَدۡ سَلَفَۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ غَفُورٗا رَّحِيمٗا ٢٣

**22-23.** ወንዶች ከሴቶች መካከል አባቶቻችሁ ያገቧቸውን አታግቡ። ያለፈው ሲቀር*። እርሱ መጥፎና የተጠላ ስራ ነውና። መንገድነቱም ከፋ (እጅግ በጣም አስከፊ መንገድ ነው)። (ወንዶች ሆይ)፣ እናቶቻችሁ፤ ሴት ልጆቻችሁም፤ እህቶቻችሁም፤ አክስቶቻችሁም፤ የእናት እህቶችም፤ (የሹሜዎቻችሁ) የወንድም ሴቶች ልጆችም፤ የእህት ሴቶች ልጆችም፤ እነዚያም ያጠቧችሁ የጡት እናቶቻችሁም የጡት እህቶቻችሁም፤ የሚስቶቻችሁም እናቶች እነዚያም ከጉያዎቻችሁ ያሉት የእነዚያ ግብረ ስጋ ግንኙነት የፈፀማችሁባቸው ሚስቶቻችሁ ሴቶች ልጆችም፤ ልታገቧቸው በእናንተ ላይ እርም ተደረጉባችሁ። ግብረ ስጋ ግንኙነት ያልፈፀማችሁባቸው የሚስቶቻችሁ ሴት ልጆቻቸውን ብታገቡ ግን በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም። የወንዶች ልጆቻችሁ ሚስቶችና ሁለት እህትማማቾችንም በአንድ መሰብሰብ እንደዚሁ እርም ነው። ከዚህ በፊት ያለፈው ሲቀር። እርሱንስ ተምራችኋል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

* ቅድመ ኢስላም (በጃሂሊያ) በተፈፀመው አትጠየቁም።

ከሴቶች ምዕራፍ (22) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡ ቀይስ የተባለው ሶሃባ ልጅ የአባቱን ሚስት ለማግባት ሲያጭ ሴትዮዋ «እኔ አንተን እንደ ልጄ ነው የማይህ» ስትል ተናገረችና«ለማንኛውም ነብዩን እጠይቃለሁ» ብላ ወደ ነብዩ በመሄድ ስለጉዳዩ ስታናግራቸው እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። እንደዚሁም አስወድ ኢብኑ ኸለፍ፤ ሶፍዋን ኢበኑ ኡመያ መንሱር ኢብኑልማሲር የተባሉ የአባቶቻቸውን ሚስት በማግባታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

۞وَٱلۡمُحۡصَنَٰتُ مِنَ ٱلنِّسَآءِ إِلَّا مَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُمۡۖ كِتَٰبَ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡۚ وَأُحِلَّ لَكُم
مَّا وَرَآءَ ذَٰلِكُمۡ أَن تَبۡتَغُواْ بِأَمۡوَٰلِكُم مُّحۡصِنِينَ غَيۡرَ مُسَٰفِحِينَۚ فَمَا ٱسۡتَمۡتَعۡتُم بِهِۦ مِنۡهُنَّ
فَـَٔاتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ فَرِيضَةٗۚ وَلَا جُنَاحَ عَلَيۡكُمۡ فِيمَا تَرَٰضَيۡتُم بِهِۦ مِنۢ بَعۡدِ ٱلۡفَرِيضَةِۚ إِنَّ
ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمٗا ٢٤

**24.** *ባል ያገቡ ሴቶችም በጦርነት እጆቻችሁ በምርኮ የያዟቸው አገልጋዮች ሲቀሩ (በእናንተ ላይ እርም ናቸው)። ይህን ህግ አላህ በእናንተ ላይ ደነገገ። ከነዚህ ከተከለከሉት ሌላ ጥብቆች ሆናችሁና ዝሙተኞች ሳትሆኑ በገንዘባችሁ ጋብቻን ልትፈልጉ ለእናንተ ተፈቀደ። እናም ከእነርሱም መገናኘት የተጠቀማችሁባቸውን ሴቶች መህሮቻቸው ግዴታ ሲሆን ስጧቸው። ከመወሰን በኋላ በተዋደዳችሁበት ነገር በእናንተ ላይ ኃጢአት የለም። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና።

✴ ክፍል አምስት

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (23-24) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሙስሊሞች ያውጧስ ዘመቻ እለት ባል ያላቸውን ሴቶች በምርኮ ይዘው ስለ ነበር «ባል እያላቸው ከእነዚህ ምርኮኛ ሴቶች ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ይፈቀዳልን?» በማለት ጥያቄ ሲያቀርቡ ምላሽ ይሆን ዘንድ ነው ይህ አን ቀፅ የወረደው። (ጦባሪ፣ ዋሒዲ፣ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَمَن لَّمۡ يَسۡتَطِعۡ مِنكُمۡ طَوۡلًا أَن يَنكِحَ ٱلۡمُحۡصَنَٰتِ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ فَمِن مَّا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُم
مِّن فَتَيَٰتِكُمُ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۚ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِإِيمَٰنِكُمۚ بَعۡضُكُم مِّنۢ بَعۡضٖۚ فَٱنكِحُوهُنَّ بِإِذۡنِ
أَهۡلِهِنَّ وَءَاتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ بِٱلۡمَعۡرُوفِ مُحۡصَنَٰتٍ غَيۡرَ مُسَٰفِحَٰتٖ وَلَا مُتَّخِذَٰتِ أَخۡدَانٖۚ
فَإِذَآ أُحۡصِنَّ فَإِنۡ أَتَيۡنَ بِفَٰحِشَةٖ فَعَلَيۡهِنَّ نِصۡفُ مَا عَلَى ٱلۡمُحۡصَنَٰتِ مِنَ ٱلۡعَذَابِۚ ذَٰلِكَ
لِمَنۡ خَشِيَ ٱلۡعَنَتَ مِنكُمۡۚ وَأَن تَصۡبِرُواْ خَيۡرٞ لَّكُمۡۗ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٢٥﴾

**25.** ከናንተ ውስጥ ጥብቆች ምዕመናትን ለማግባት ሀብትን ያልቻለ ሰው እጆቻችሁ ንብረት ካደረጓቸው ከምዕመናት መካከል ወጣቶቻችሁን አገልጋዬች (ወይዛዝርት) የመረጠውን ያግባ። አላህ የውስጥ እምነታችሁን ምንነት አዋቂ ነውና። ከፊላችሁ ከከፊሉ የተራባ ነው። ባሮችንም እንደዚሁ በአሰሪዎቻቸው ፈቃድ ብቻ አግቧቸው። መህሮቻቸውንም በመልካም መንገድ ስጧቸው። ጥብቆች ሆነው ዝሙተኛ ያልሆኑ የስርቆሽ ወዳጅንም ያልያዙ እንደሆኑ ብቻ አግቧቸው። በማግባት በተጠበቁም ጊዜ መጥፎን ስራ ቢሰሩ በእነርሱ ላይ ከቅጣት በነፃዎች ላይ የተደነገገ ቅጣት ግማሽ ቅጣት አለባቸው። ይኼ (ባሪያን ማግባት) ከናንተ ዝሙትን ለፈራ ሰው ብቻ ነው። መታገሳችሁ የተሻለ ነው። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

يُرِيدُ ٱللَّهُ لِيُبَيِّنَ لَكُمۡ وَيَهۡدِيَكُمۡ سُنَنَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ وَيَتُوبَ عَلَيۡكُمۡۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ
حَكِيمٞ ﴿٢٦﴾ وَٱللَّهُ يُرِيدُ أَن يَتُوبَ عَلَيۡكُمۡ وَيُرِيدُ ٱلَّذِينَ يَتَّبِعُونَ ٱلشَّهَوَٰتِ أَن تَمِيلُواْ مَيۡلًا
عَظِيمٗا ﴿٢٧﴾ يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُخَفِّفَ عَنكُمۡۚ وَخُلِقَ ٱلۡإِنسَٰنُ ضَعِيفٗا ﴿٢٨﴾

**26-28.** (አማኞች ሆይ)፣ አላህ የሃይማኖታችሁን ህግጋት ከናንተ በፊትም የነበሩትን ነብያት ፈለጎች ሊያብራራላችሁ በእናንተም ላይ ፀፀትን ሊቀበል ይሻል። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው። አላህ በእናንተ ላይ ፀፀትን ሊቀበል ይሻል። እነዚያ ፍላጎታቸውን የሚከተሉ ሰዎች ግን ከእውነት ትልቅን መዘንበል እንድትዘነበሉ ይፈልጋሉ። አላህ ከናንተ ሊያቃልላችሁ ይሻል። ምክንያቱም ሰው ደካማ ሆኖ የተፈጠረ ነውና።

**ሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (15-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኢስላም ልጅ አባቱ ሲሞት የአባቱን ሚስት እንዲወርስ የሚፈቅደው የጃሂሊያ (የመሀይምነት) ስርዓት የተከለከለ መሆኑን፤
2. በኢስላም ሴት ልጅ ገንዘቧን ለማስመለስ በማቀድ ማስጨነቅና የተከለከለ እንደሆነ፤
3. በኢስላም ትዕግስት እጅግ አስፈላጊና መልካም ስነ. ምግባር እንደሆነ፤
4. በኢስላም በግልፅ ዝሙት የፈፀሙች ሴት ለባሏ የገንዘብ ክፍያውን ፈፅማ ኃብቻዋን ማፍረስ አለባት።
5. በኢስላም የጋብቻ ጥሎሹን መጠን ዝቅተኛ ማድረጉ በኢስላም ተመራጭና በላጭ ቢሆንም ብዙ መጠን ያለው መህር (ጥሎሽ) በጭራሽ የተከለከለ ነው።
6. ሌላ ችግር እስከሌለው ድረስ ጥሎሹ ቢበዛም ክልክል እንዳልሆነ እንማራለን።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَأْكُلُوٓا۟ أَمْوَٰلَكُم بَيْنَكُم بِٱلْبَـٰطِلِ إِلَّآ أَن تَكُونَ تِجَـٰرَةً عَن
تَرَاضٍ مِّنكُمْ ۚ وَلَا تَقْتُلُوٓا۟ أَنفُسَكُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِكُمْ رَحِيمًا ﴿٢٩﴾ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ
عُدْوَٰنًا وَظُلْمًا فَسَوْفَ نُصْلِيهِ نَارًا ۚ وَكَانَ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرًا ﴿٣٠﴾

**29-30.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ገንዘቦቻችሁን በመካከላችሁ ያለ አግባብ አትብሉ። በእናንተ መካከል በመዋደድ የሆነችውን ንግድ ግን (ብሉ)። ነፍሶቻችሁን በራሳችሁ አትግደሉ።* አላህ ለእናንተ አዛኝ ነውና። ወሰን በማለፍ እና በመበደል ይህን የሰራ ሰው ሁሉ እሳት እናስገባዋለን። ይህም በአላህ ላይ ገር ነውና።

* ሳቢት ኢብኑ አድ ደሓክ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት፡- ነብዩ እንዲህ ብለዋል፡- «ራሱን አፍኖ የገደለ ሰው እሳት ውስጥ ራሱን ያፍናል። ራሱን ወግቶ የገደለ ሰው በእሳት ውስጥ ራሱን ይወጋል።

إِن تَجْتَنِبُوا۟ كَبَآئِرَ مَا تُنْهَوْنَ عَنْهُ نُكَفِّرْ عَنكُمْ سَيِّـَٔاتِكُمْ وَنُدْخِلْكُم مُّدْخَلًا كَرِيمًا ﴿٣١﴾
وَلَا تَتَمَنَّوْا۟ مَا فَضَّلَ ٱللَّهُ بِهِۦ بَعْضَكُمْ عَلَىٰ بَعْضٍ ۚ لِّلرِّجَالِ نَصِيبٌ مِّمَّا ٱكْتَسَبُوا۟ ۖ وَلِلنِّسَآءِ
نَصِيبٌ مِّمَّا ٱكْتَسَبْنَ ۚ وَسْـَٔلُوا۟ ٱللَّهَ مِن فَضْلِهِۦٓ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمًا ﴿٣٢﴾

**31-32.** ከተከለከላችሁት ወንጀሎች ታላላቆችን ብትርቁ ትናንሽ ኃጢአቶችን*1 እናብስላችኋለን። የተከበረውንም ገነት እናስገባችኋለን። አላህ ከፊላችሁን በከፊሉ ያበለጠበትን ፀጋ አትመኙ። ለወንዶችም ከሰሩት ስራ እድል አለላቸው። ለሴቶችም ከሰሩት ስራ እንዲሁ እድል አለላቸው*2። አላህን ከችሮታው ለምኑት። አላህ በሁሉ ነገር አዋቂ ነውና።

*1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ሰባት ከበባድ ወንጀሎችን ራቁ» ሶሓባዎችም«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነዚህ ሰባቱ ከበባድ ወንጀሎች ምን ምን ናቸው?» ሲሉ ጠየቁ። እሳቸውም፦

1. በአላህ ማጋራት፤
2. ድግምት መስራት፤
3. አላህ ክልክል ያደረገውን ነፍስ ያለ አግባብ ማጥፋት፤
4. ወለድ መብላት፤
5. የሙት ልጆችን ገንዘብ መብላት፤
6. በጦርነት ላይ ለጠላት ጀርባ መስጠትና ማፈግፈግ፤
7. ጥብቅ የሆኑ ሙዕሚን እንስቶችን በዝሙት ወንጀል ስማቸውን ማጥፋት»

*2 አላህ ሰዎችን ሲፈጥር ሁሉንም እኩል አድረጎ ነው የፈጠራቸው። ሴትን ከወንድ አሳንሶ ሳይሆን የፈጠራት የራስዋ የሆነን ተግባርና ግዴታ ሰጥቶ ነው። ወንድንም ሲፈጥር እንደዚሁ ከሴት አብልጦ ሳይሆን ለራሱ አፈጣጠርና አካላዊም ሆነ አዕምሯዊ ሁኔታው ተስማሚ አድርጎ ነው የፈጠረው። ስለዚህ ወንድ የሴትን ሴትም የወንድን ድርሻ ለመውሰድ መመኘት አይገባትም። ስለዚህ ሴትና ወንድ ተመሳሳይ ሳይሆኑ እኩል ናቸው። ተመሳሳይነት የማይቻልና ለየትኛውም ፆታ የማይጠቅም፤ ወንድም ሆነ ሴትን ተመሳሰሉ ቢባል የማይቻል ነገርን ማስገደድ ነው።

ከሴቶች ምዕራፍ (32) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ከእነዚህ አናቅፅ ውስጥ የተወሰኑት ቁርአናዊ አናቅፅ ኡሙ ሰለማ የተባሉ የነብዩ (ﷺ) ባለቤት ሶሀብያ «በወንዶች ላይ ዘመቻ ግዳጅ ሆኖ ሲዘምቱ እኛስ ለምን አንዘምትም! ለምንስ በውርስ ወቅት የወንድ ግማሽ ብቻ እንድንወርስ ተደነገገ። ብለው ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ወረደ። (ቲርሚዚ፤ ሓኪም፤ ዋሒዲ)

وَلِكُلٍّ جَعَلْنَا مَوَٰلِىَ مِمَّا تَرَكَ ٱلْوَٰلِدَانِ وَٱلْأَقْرَبُونَ ۚ وَٱلَّذِينَ عَقَدَتْ أَيْمَـٰنُكُمْ فَـَٔاتُوهُمْ نَصِيبَهُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ شَهِيدًا ﴿٣٣﴾

**33.** ለሁላችሁም ወላጆችና የቅርብ ዘመዶች ከተውት ሀብት ጠቅላይ ወራሾችን አድርገናል። እነዚያንም (ለመረዳትና ለመዋረስ) በመሐላዎቻችሁ የተዋዋላችኋቸውን (ከስድስት አንድ) ድርሻቸውን ስጧቸው። አላህ በነገሩ ሁሉ አዋቂ (መስካሪ) ነው።

ከሴቶች ምዕራፍ (33) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዐረቦች ልጆቻቸው ያልሆኑትን ከገንዘባቸው እንዲወርሱ ያደርጉ ስለ ነበር ነው። ይህ አንቀፅ የወረደው።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (29-33) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ይህ ህግ ማለትም በመሀላ (በኑዛዜ) የመዋረሱ ጉዳይ በውርስ አንቀፅ በተደነገገው ስርዐተ ውርስ ህግ ተሸሯል።
2. በኢስላም በትዳር ላይ ያለች ሴት ሁለተኛ ባል ማግባት ቀርቶ መደራደር እንኳን የተከለከለ መሆኑን፤
3. በኢስላም የተገዛች ባሪያ (በምርኮ የተገኘች) ሴት ቀደም ብሎ ያገባት ባል የነበራት ቢሆንም እንኳን ውሉ ስለሚፈርስ የገዛት (የማረካት) እሷን ማግባት የተፈቀደለት መሆኑን፤
4. በኢስላም መህር መስጠት ግዴታ መሆኑና ሴቷ ግን የመህሩን ገንዘብ ከፈለገች ለባሏ መስጠት የምትችል መሆኑን፤
5. በኢስላም ባሪያዎች የዝሙትን ወንጀል ከፈፀሙ ልክ እንደ ነፃው ሰው ምድራዊ ቅጣት ሊፈፀምባቸው እንደሚገባ።
6. አላህ ህግጋትን ሲደነግግ የድንጋጌዎችን ምክንያት በማብራራት ጭምር መሆኑንና ይህም ታላቅ የሆነ ውለታ እንደሆነ፤
7. አላህ አማኞች የመልካም ሰዎችን አርአያ እንዲከተሉ ማድረጉም ለሰው ልጆች ከዋላቸው ውለታዎች እንደሚቆጠርና እንዲሁም አማኞችን ልቦቻቸው ከመጥፎ ነገሮች እንዲፀዱ ማድረጉም የእርሱ ውለታ እንደሆነ፤
8. የሰው ልጅ በተፈጥሮው መጥፎም ይሁን ጥሩ ባህሪ ቢኖረው ሌሎች ሰዎች እሱን እንዲመስሉ የሚመኝ መሆኑን፤
9. የሰው ልጅ በአፈጣጠሩ ስሜቱን መቆጣጠር እንኳ የማይችል ደካማ ፍጡር መሆኑን፤
10. የሙስሊሞች ገንዘብና ንብረት ያለ አግባብ መውሰድ (መዝረፍ) የተከለከለ መሆኑን፤
11. በኢስላም ሰው የምድራዊ ሕይወቱን መሰረታዊ ፍላጎቶች ለማሟላት ስራ ወሳኝ በመሆኑ የንግድ ስራ የተፈቀደ ስራ መሆኑን፤
12. ሙስሊም የራሱንም ነፍስ ሆነ የሌላ ሙስሊም ወንድሙን ነፍስ ማጥፋት የተከለከለ መሆኑን፤
13. ከታላላቅ ወንጀሎች መራቅ ኢስላማዊ ግዴታ መሆኑን፤
14. በኢስላም ወንጀሎች በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላሉ።
15. ጀነትን ለመውረስ የምታበቃዋ ነፍስ ከክህደት ከአመፅና ከአስመሳይነት የጠራችዋ ንፁህ ነፍስ ናት።
16. በኢስላም በተግባር የማይተረጎም ባዶ ምኞት የተወገዘ ብልሹ ምግባር መሆኑን፤
17. ምቀኝነት ከመጥፎ ባህሪያቶች ዋነኛው እንደሆነና መመቅኘት በኢስላም የተከለከለ ነው።
18. ፀሎት (ዱዓ) ከታላላቅ የዒባዳ ተግባራት አንዱ መሆኑን፤
19. ውርስ ከማህበራዊ ጉዳዩች ውስጥ የሚካተት እንደመሆኑ በኢስላም የራሱ የሆነ ህግ የወጣለት መሰረታዊ ጉዳይ መሆኑን፤
20. በኢስላም በሁሉም የእንቅስቃሴ ዓይነቶች፤ የሕይወት ጎዞዎች አላህን መፍራት ተገቢ መሆኑን፤
21. ባሎቻቸው ከሀገር በራቁ ጊዜ መብታቸው እንዳይደፈርና ገንዘባቸውም እንዳይባክን ጠባቂዎች ሴቶች መሆኑን፤

ٱلرِّجَالُ قَوَّٰمُونَ عَلَى ٱلنِّسَآءِ بِمَا فَضَّلَ ٱللَّهُ بَعۡضَهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖ وَبِمَآ أَنفَقُواْ مِنۡ أَمۡوَٰلِهِمۡۚ فَٱلصَّٰلِحَٰتُ قَٰنِتَٰتٌ حَٰفِظَٰتٞ لِّلۡغَيۡبِ بِمَا حَفِظَ ٱللَّهُۚ وَٱلَّٰتِي تَخَافُونَ نُشُوزَهُنَّ فَعِظُوهُنَّ وَٱهۡجُرُوهُنَّ فِي ٱلۡمَضَاجِعِ وَٱضۡرِبُوهُنَّۖ فَإِنۡ أَطَعۡنَكُمۡ فَلَا تَبۡغُواْ عَلَيۡهِنَّ سَبِيلًاۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيّٗا كَبِيرٗا ٣٤

34. ወንዶች ለሴቶች ቋሚና የበላይ አስተዳዳሪዎች ናቸው። አላህ ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ በማብለጡና (ወንዶች) ከገንዘቦቻቸው (ለሴቶች) በመስጠታቸው ነው። መልካሞቹ ሴቶች ማለት ለባሎቻቸው ታዛዦች፤ አላህ ባስጠበቀው ነገር ከባሎቻቸው ሩቅ የሆነውን ጠባቂዎች ናቸው። እነዚያን ማመፃቸውን የምትፈሩትን ሴቶች መጀመሪያ ገስጿቸው። ከዚያም በመኝታቸው ተለዩዋቸው። ከዚያም በአካሎቻቸው ላይ ሳካ ሳታደርሱ ምቷቸው። ከታዘዟችሁ ለመጨቆን ስትሉ በእነርሱ ላይ መንገድን አትፈልጉ። አላህ የበላይና ታላቅ ነውና።

ከሴቶች (34) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰዕድ ቢን ረቢዕ የተባለው ሶሃባ ሚስቱ አስቸግራው ስለ ነበር ለመቅጣት በማሰብ በጥፊ ሲመታት ከአባቷ ጋር በመሆን ወደ ነብዩ ስሞታ ለማቅረብ መጣች። አባቷ የምወዳትን ልጅ ድሬው ሳለ በጥፊ መታት ሲሉ አቤቱታ አቀረቡ። ነብዩም (ﷺ) ለተመታችው ጥፊ በቀል የሚሆን ቅጣት ይሰጠዋል በማለት ወሰኑና ወደ ቤታቸው ለመመለስ መንገድ ከጀመሩ በኋላ ተመለሱና ይኸው ጅብሪል መልሱን ይዞ መጣ አሉ። ከዚያም አላህ ትክክለኛውን ነገር ለማስረዳት ከላይ ከተጠቀሱ አናቅፅ ጋር አያይዞ የተወሰኑትን አናቅፅ ለዚህ ጉዳይ አወረደ። በነብዩ እኛ አንድ ነገር አሰበን አላህ ደግሞ ሌላ አሰበ። እናም አላህ ያሰበው ይበልጣል አሉ። በዚህም ቂሷስ ቀረ። (ጦበሪ፤ ዋሒዲና ሱዩጢ)

وَإِنۡ خِفۡتُمۡ شِقَاقَ بَيۡنِهِمَا فَٱبۡعَثُواْ حَكَمٗا مِّنۡ أَهۡلِهِۦ وَحَكَمٗا مِّنۡ أَهۡلِهَآ إِن يُرِيدَآ إِصۡلَٰحٗا يُوَفِّقِ ٱللَّهُ بَيۡنَهُمَآۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا خَبِيرٗا ٣٥

35. እናንተ ቤተሰቦች ሆይ፣ በመካከላቸው ጭቅጭቅ መኖሩን ብታውቁ ከቤተሰቡና ከቤተሰቦቿ የተውጣጡ የቤተ ዘመድ ጉባኤ አዋቅሩ። እርቅ ቢሹ አላህ በመካከላቸው ያስማማቸዋል። አላህ ግልፅንም ሆነ ውስጥን አዋቂ ነውና።

۞ وَٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَلَا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗا وَبِذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱلۡجَارِ ذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡجَارِ ٱلۡجُنُبِ وَٱلصَّاحِبِ بِٱلۡجَنۢبِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِ

وَمَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُمۡۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ مَن كَانَ مُخۡتَالٗا فَخُورًا ٣٦ ٱلَّذِينَ يَبۡخَلُونَ وَيَأۡمُرُونَ ٱلنَّاسَ بِٱلۡبُخۡلِ وَيَكۡتُمُونَ مَآ ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ وَأَعۡتَدۡنَا لِلۡكَٰفِرِينَ عَذَابٗا مُّهِينٗا ٣٧ وَٱلَّذِينَ يُنفِقُونَ أَمۡوَٰلَهُمۡ رِئَآءَ ٱلنَّاسِ وَلَا يُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَلَا بِٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۗ وَمَن يَكُنِ ٱلشَّيۡطَٰنُ لَهُۥ قَرِينٗا فَسَآءَ قَرِينٗا ٣٨

**36-38.** ሰዎች ሆይ፣ አላህን ተገዙ። በእርሱ ምንም አታጋሩ። ለወላጆች፤ ለቅርብ ዝምድና ባለቤቶችም፤ ለየቲሞችም ለምስኪኖችም፤ ለቅርብ ጎረቤትም ሆነ ለሩቅ ጎረቤት፤ ለጎን ባልደረባም፤ ለመንገደኛም፤ እጆቻችሁ ንብረት ላደረጓቸውም ባሮች መልካምን ስራ ስሩ። አላህ ኩራተኞችንና ጉረኞችን አይወድምና። እነዚያ የሚሰስቱ ንፉጎችና ሰዎችንም በመሰሰት (በንፍግና) የሚያዝዙ አላህ በችሮታው የሰጣቸውን ፀጋ የሚደብቁ (ብርቱን ቅጣት ይቀጣቸዋል)። ለከሓዲያንም አዋራጅን ቅጣት* አዘጋጅተናል። እነዚያ ለሰዎች ለመታየት ሲሉ ገንዘቦቻቸውን የሚሰጡ በአላህ እና በመጨረሻው ቀን የማያምኑ (ይቀጣሉ)። ሰይጣንም የእሱ ጓደኛው የሆነ ሰው ሁሉ ጓደኛነቱ ከፉ!

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «በየቀኑ ከሰማይ ሁለት መላእክት ይወርዳሉ። ከነዚህ መላእክት መካከል አንዱ አላህ ሆይ! በአንተ መንገድ ገንዘባቸውን ለሚሰጡ መተኪያ አድርግላቸው ሲል ሌላናው ደግሞ አላህ ሆይ! ሁሉንም ንፉግ አጥፋ ይላል»

وَمَاذَا عَلَيۡهِمۡ لَوۡ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَأَنفَقُواْ مِمَّا رَزَقَهُمُ ٱللَّهُۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِهِمۡ عَلِيمًا ٣٩ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَظۡلِمُ مِثۡقَالَ ذَرَّةٖۖ وَإِن تَكُ حَسَنَةٗ يُضَٰعِفۡهَا وَيُؤۡتِ مِن لَّدُنۡهُ أَجۡرًا عَظِيمٗا ٤٠

**39-40.** በአላህና በመጨረሻው ቀን በአመኑ አላህ ከሰጣቸውም ሲሳይ በለገሱ ኖሮ በእነርሱ ላይ ምን ጉዳት ነበረ? አላህ በእነርሱ ሁኔታ አዋቂ ነውና። አላህ የብናኝን* ክብደት ያህል እንኳን አይበድልም። መልካም ስራ ብትሆንም ይደራርባታል። ከእነርሱም ዘንድ ታላቅን ምንዳ ይሰጣል:

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒድ አል. ኹድሪ እንዳስተላለፉት ነብዩ ዘመን የነበሩ ሰዎች «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጌታችንን በትንሳኤ ቀን እናየዋለን?» አሉ። ነብዩም «አዎን» ሰማይ ደመና ሳይኖረው ጥርት ባለበት የእኩለ ቀን ላይ ፀሐይን ለማየት ትቸገራላችሁን?» በማለት የሰዎችን ጥያቄ በጥያቄ መልክ መልሰው ሰዎችን ሲጠይቁ፤ ሰዎቹም «በፍፁም አንቸገርም» በማለት መለሱላቸው። እሳቸውም «ሰማይና ደመና ሳይኖረው ጥርት ባለበት ለሊት ሙሉ ጨረቃን ለማየት ትቸገራላችሁን? በማለት በድጋሚ ጠየቁ። ሰዎችም «በፍፁም አንቸገርም» በማለት መለሱ። ነብዩም እንዲህ አሉ፤

«ልክ እነርሱን ለማየት እንደማትቸገሩት ሁሉ በትንሳኤ ቀን አላህን ለማየት አትቸገሩኝ። በትንሳኤ ቀን «ሁሉም ሕዝብ ያመልከው የነበረውን አምልኮ ይከተል» በማለት ጥሪውን ያስተጋባል። አላህን ይገዛ የነበረ መልካምም ሆነ መጥፎ ሰው (ከመፅሐፍ ባለቤቶች በቀር) ከአላህ ሌላ ሲመለኩ የነበሩ ጣኦታትና ምስሎች በሙሉ ወደ እሳት ይወረወራሉ። አይሁዶች ተጠርተው «ምንድን ነበር ስታመልኩ የነበራችሁት?» ይባላሉ። «ዑዘይርን የአላህ ልጅን እናመልክ ነበር» ይላሉ። «ሀሰት ተናግራችኋል፤ አላህ ባለንግም ሆነ ልጅ አልያዘም፤ ምን ትሻላችሁ ይባላሉ። «ጌታችን ሆይ! ተጠምተናልና አጠጣን» ይላሉ። ወደዚያም ይመሩናል «ለመጠጣት አትፈልጉምን?» ይባላሉ። ወደ እሳትም ይሰባሰባሉ። ያች እለት ልክ እርስ በርሱ እንደሚማታ ሚራዥ ነች። በዚያ ውስጥም አንድ በአንድ ይወድቃሉ። ከዚያም ክርስቲያኖች ይጠራሉ «ምንድን ታመልኩ ነበር?» ተብለው ይጠየቃሉ። «መሲሕን የአላህን ልጅን እናመልክ ነበር» ይላሉ። «ሀሰት ብላችኋል፤ አላህ ባላንጣም ሆነ ልጅ አልያዘም፤ አሁንም ምን ትፈልጋላችሁን» ይባላል። ከነርሱ ቀደም ያሉት ሰዎች የጠየቁትን ይጠይቃሉ። ላይ እንደተፈፀመው እነርሱም ወደ እሳት ይወረወራሉ። ከዚያም አላህን ብቻ ሲያመልኩ የነበሩ መልካምና መጥፎ ሰዎች ይቀራሉ። የዓለማት ጌታ አላህ ሰዎች ቀድሞ ካዩት መልኩ ባነሰ ሁኔታ ተገልጦ ይታያቸዋል። «ምንስ ትጠብቃላችሁ። ሁሉም ሕዝቦች ያመልኩት የነበረውን ተከትለው ሄደዋል አይደለምን?» ይባላሉ። እነርሱም «በምድር ላይ በጣም ቀርበናቸው ከነበሩት ሰዎች ጋር ተለያይተናል፤ አሁንም አልተጎዳኘናቸውም። ስለዚህ ስናመልከው የነበረውን ጌታችንን ነው የምንጠብቀው» ይላሉ። አላህም «እኔ ጌታችሁ ነኝ» ይላል። እነሱም ሁለት ወይም ሶስት ጊዜ «በአላህ አንዳች ነገርን አናጋራም» ይላሉ»

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (37-40) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የነብዩን ማንነት የደበቁትን አይሁድን ለመውቀስ እና ለማጋለጥ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ኢብኑልጀውዚ)

فَكَيْفَ إِذَا جِئْنَا مِن كُلِّ أُمَّةٍ بِشَهِيدٍ وَجِئْنَا بِكَ عَلَىٰ هَٰٓؤُلَآءِ شَهِيدًا ﴿٤١﴾ يَوْمَئِذٍ يَوَدُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَعَصَوُا۟ ٱلرَّسُولَ لَوْ تُسَوَّىٰ بِهِمُ ٱلْأَرْضُ وَلَا يَكْتُمُونَ ٱللَّهَ حَدِيثًا ﴿٤٢﴾

**41-42.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሕዝቦች ሁሉ መስካሪን ባመጣንና አንተንም በእነዚህ በአንተ ህዝቦች በመስካሪዎች ላይ መስካሪ አድርገን በምናመጣህ ጊዜ የከሐዲያንን ሁኔታ እንዴት ይሆን? በዚያ ቀን እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎችና መልዕክተኛውን ያልታዘዙት በእነርሱ ምድር ብትደፋባቸው ይመኛሉ። ከአላህም አንድን ወሬን አይደብቁም።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَقْرَبُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنتُمْ سُكَٰرَىٰ حَتَّىٰ تَعْلَمُوا۟ مَا تَقُولُونَ وَلَا جُنُبًا إِلَّا عَابِرِى سَبِيلٍ حَتَّىٰ تَغْتَسِلُوا۟ ۚ وَإِن كُنتُم مَّرْضَىٰٓ أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ أَوْ جَآءَ أَحَدٌ مِّنكُم مِّنَ ٱلْغَآئِطِ أَوْ لَٰمَسْتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَلَمْ تَجِدُوا۟ مَآءً فَتَيَمَّمُوا۟ صَعِيدًا طَيِّبًا فَٱمْسَحُوا۟ بِوُجُوهِكُمْ وَأَيْدِيكُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَفُوًّا غَفُورًا ﴿٤٣﴾

43. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! እናንተ የሰከራችሁ ሆናችሁ የምትሉትን ነገር እስከምታውቁ ድረስ ወደ ሶላት አትቅረቡ። ጀናባ ስትሆኑ መንገድን አላፊዎች ካልሆናችሁ በስተቀር አካላታችሁን እስከምትታጥቡ ድረስ ስግደትን አትቅረቡ። በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትሆኑ ወይም ከናንተ አንዱ ከአይነ ምድር ቢፀዳዳ ወይም ከሴቶች ጋር የግብረስጋ ግንኙነት ብትፈፅሙና ውሃን ባታገኙ ንፁህ የሆነን የምድር ገፅ (አፈርን) አብሱ። ከዚያ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁን በእርሱ አብሱ። አላህ ይቅር ባይና መህሪ ነውና።

ከሴቶች ምዕራፍ (43) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በእመቤት አይሻ ጌጥ መጥፋት የተነሳ ከጉዞዋቸው በመዘግየታቸው ያለ ውሃ ሶላት ሰለ ደረሰባቸው ሲጨነቁ በነበሩ ሙስሊሞች ምክንያት ነው የወረደው። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ቁርጡቢ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ أُوتُواْ نَصِيبٗا مِّنَ ٱلۡكِتَٰبِ يَشۡتَرُونَ ٱلضَّلَٰلَةَ وَيُرِيدُونَ أَن تَضِلُّواْ
ٱلسَّبِيلَ ٤٤ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِأَعۡدَآئِكُمۡۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَلِيّٗا وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ نَصِيرٗا ٤٥

44-45. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ ከመጽሐፉ የእውቀት እድልን ወደ ተሰጡት ክፍሎች አላየህምን? ጥመትን በቅንነት ይገዛሉ። መንገድንም እንድትሳሳቱ ይፈልጋሉ። (አማኞች ሆይ)፤ አላህ ጠላቶቻችሁን ከናንተ በበለጠ አዋቂ ነው። ጠባቂነትም በአላህ በቃ። ረዳትነትም በአላህ በቃ።

مِّنَ ٱلَّذِينَ هَادُواْ يُحَرِّفُونَ ٱلۡكَلِمَ عَن مَّوَاضِعِهِۦ وَيَقُولُونَ سَمِعۡنَا وَعَصَيۡنَا وَٱسۡمَعۡ غَيۡرَ
مُسۡمَعٖ وَرَٰعِنَا لَيَّۢا بِأَلۡسِنَتِهِمۡ وَطَعۡنٗا فِي ٱلدِّينِۚ وَلَوۡ أَنَّهُمۡ قَالُواْ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَا وَٱسۡمَعۡ
وَٱنظُرۡنَا لَكَانَ خَيۡرٗا لَّهُمۡ وَأَقۡوَمَ وَلَٰكِن لَّعَنَهُمُ ٱللَّهُ بِكُفۡرِهِمۡ فَلَا يُؤۡمِنُونَ إِلَّا قَلِيلٗا ٤٦

46. ከእነዚያ ከአይሁዳውያን መካከል ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ ክፍሎች አሉ። ሰማንና አመፅን የማትሰማም ስትሆን ስማ ይላሉ። በምላሶቻቸውም ለማጣመምና ሃይማኖትንም ለመዝለፍ ራዒና ይላሉ። እነርሱም ሰማንና ታዘዝን ስማ ተመልከተንም ባሉ ኖሮ ለእነርሱም መልካምና ትክክለኛ በሆነ ነበር። ግን በክህደታቸው ምክንያት አላህ ረገማቸው። ከእነርሱም መካከል ጥቂቶች እንጂ በትክክል አያምኑም።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ ءَامِنُواْ بِمَا نَزَّلۡنَا مُصَدِّقٗا لِّمَا مَعَكُم مِّن قَبۡلِ أَن نَّطۡمِسَ
وُجُوهٗا فَنَرُدَّهَا عَلَىٰٓ أَدۡبَارِهَآ أَوۡ نَلۡعَنَهُمۡ كَمَا لَعَنَّآ أَصۡحَٰبَ ٱلسَّبۡتِۚ وَكَانَ أَمۡرُ ٱللَّهِ مَفۡعُولًا ٤٧

**47.** እናንተ መጽሐፉ የተሰጣችሁ ሰዎች ሆይ፣ ፊቶችን ሳናብስና በጀርባዎች ላይ ሳንመልሳቸው ወይም የሠንበትን ባለቤቶች እንደረገምን ሳንረግማችሁ በፊት ከናንተ ጋር ያለውን የሚያረጋግጥ ሆኖ በአወረድነው ቁርኣን እመኑ። የአላህም ትዕዛዝ ተፈፃሚ ነው።

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغْفِرُ أَن يُشْرَكَ بِهِۦ وَيَغْفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُ ۚ
وَمَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدِ ٱفْتَرَىٰٓ إِثْمًا عَظِيمًا ﴿٤٨﴾

**48.** አላህ በእርሱ ማጋራትን ፈፅሞ አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውን ኃጢአት* ግን ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህ የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኃጢአት በእርግጥ ቀጠፈ።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል:- «በጀሀነም ውስጥ በጣም ዝቅተኛው ቅጣት ለሚቀጣው ሰው «በምድር ላይ ያለው ነገር ሁሉ ቢኖርህ ራስህን ከጀሀነም ቅጣት ነፃ ለማውጣት ስትል አሳልፈህ ትሰጣለህን?» ተብሎ ይጠየቃል። ሰውዬውም «አዎን!» በማለት ይመልሳል። አላህም «አንተ በአደም የጀርባ አጥንት ላይ ሳለህ ከዚህ በጣም ያነሰ ነገር ጠይቄህ ነበር። ይኸውም በእኔ ላይ እንዳታጋራ ነበር። አንተ ግን እምቢኝ ብለህ በማጋራት ላይ ሙጭጭ አልክ»።»

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ يُزَكُّونَ أَنفُسَهُم ۚ بَلِ ٱللَّهُ يُزَكِّى مَن يَشَآءُ وَلَا يُظْلَمُونَ فَتِيلًا ﴿٤٩﴾
ٱنظُرْ كَيْفَ يَفْتَرُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ ۖ وَكَفَىٰ بِهِۦٓ إِثْمًا مُّبِينًا ﴿٥٠﴾

**49-50.** ወደ እነዚያ ነፍሶቻቸውን ወደ ሚያጠሩት (ሚያወድሱት) አላየህምን?። አይደለም አላህ የሚፈልገውን ያጠራል። በተምር ፍሬ ስንጥቅ ላይ ያለችን ክር መሳይ* ያህልም አይበደሉም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ላይ ውሸትን እንዴት እንደሚቀጥፉ ተመልከት። ይህ ግልፅና በቂ ወንጀል ነው።

✷ በዚህ አንቀፅ ላይ ፈቲል የሚለው፤ በ (53) ኛው እና በ (124) ኛው አንቀፅ ላይ ያለው ነቂርና በፋጢር (13) ኛ ላይ ያለው ቂጥሚር የሚሉት ሶስቱም በቴምር ላይ ያሉ ተአምር ነገሮች ናቸው።

ከሴቶች ምዕራፍ (49) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የተወሰኑ አይሁዶች ህፃን ልጆች ይዘው ወደ ነብዩ በመምጣት «ሙሐመድ ሆይ! እነዚህ ህፃናት ላይ ወንጀል አለን? በማለት ጠየቋቸው። አይቀጡም ሲሏቸው» «ታዲያ እኛስ ልክ እንደነሱ አይደለን ሁልጊዜ በቀን የምንሰራው ሁሉ ሌሊት ይሰረዝልናል»፤ በሌሊት የምንሰራው ሁሉ በቀን ይሰረዝልናል በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑል ጀውዚ እና ሱዩጢ)

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ نَصِيبًا مِّنَ ٱلْكِتَٰبِ يُؤْمِنُونَ بِٱلْجِبْتِ وَٱلطَّٰغُوتِ وَيَقُولُونَ لِلَّذِينَ
كَفَرُوا۟ هَٰٓؤُلَآءِ أَهْدَىٰ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ سَبِيلًا ﴿٥١﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَعَنَهُمُ ٱللَّهُ ۖ
وَمَن يَلْعَنِ ٱللَّهُ فَلَن تَجِدَ لَهُۥ نَصِيرًا ﴿٥٢﴾

**51-52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ ከመጽሐፍ እድልን ወደ ተሰጡት አላየህምን? በድግምትና በጣዖት ያምናሉ። ለእነዚያ በአላህ ለካዱት:- እናንተ በመንገድ (በሃይማኖት) ከእነዚያ ካመኑት ይበልጥ የቀናችሁ ናችሁ ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ አላህ የረገማቸው ናቸው። አላህ የረገመው ሰው ደግሞ ለእርሱ ፈፅሞ ረዳትን አታገኝለትም።

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (51-52) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- የመካ መሪ የነበረው አቡሱፍያን ለካዕብ ቢን አሽረፍ እና ሁየይ ኢኢብኑ አኽጠብ ለተባሉ የአይሁድ መሪዎች «እናንተ መፅሐፍትን ያነበባችሁ ምሁራን (አዋቂ) ናችሁ። እኛ ደግሞ መሀይማን ነን። ስለሆነም ከእኛና ከሙሐመድ እምነት የትኛው ይሻላል? የትኛችንስ በቀናው መንገድ ላይ ቆመናል? ብሎ ጠየቃቸው ካዕባ ኢብኑ አሽረፍም እስኪ እምነታችሁን ግለፁልኝ» በማለት ጥያቄውም በጥያቄ መለሰ። አቡሱፍያንም «ለሐጃጆች እናበላለን፤ እናጠጣለን፤ የአላህን ቤት እንገነባለን፤ ሙሐመድ ግን የአባቶቹን እምነት ትቷል። ዝምድናን ቆርጧል» አለ። ካዕብ ቢን አሽረፍ የእናንተ እምነት ከሙሐመድ እምነት የተሻለ እና እናንተም በቀጥተኛው መንገድ ላይ ናችሁ።» በማለት ሲመልስ ይህ አባባል ምን ያህል ስህተት እንደሆነ ለመግለፅ ነው አናቅፅ የወረዱት። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَمۡ لَهُمۡ نَصِيبٞ مِّنَ ٱلۡمُلۡكِ فَإِذٗا لَّا يُؤۡتُونَ ٱلنَّاسَ نَقِيرًا ٥٣ أَمۡ يَحۡسُدُونَ ٱلنَّاسَ عَلَىٰ مَآ
ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۖ فَقَدۡ ءَاتَيۡنَآ ءَالَ إِبۡرَٰهِيمَ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَءَاتَيۡنَٰهُم مُّلۡكًا
عَظِيمٗا ٥٤ فَمِنۡهُم مَّنۡ ءَامَنَ بِهِۦ وَمِنۡهُم مَّن صَدَّ عَنۡهُۚ وَكَفَىٰ بِجَهَنَّمَ سَعِيرًا ٥٥

**53-55.** በእውነቱ ለእነርሱ ከንግስናው ፈንታ አላቸውን? ያን ጊዜ ለሰዎች በተምር ፍሬ ላይ ያለችውን ነጥብ ያህል አይሰጡም ነበር። ይልቁንም ለሰዎች አላህ ከችሮታው ከሰጣቸው ነገር ላይ ይመቀኛሉን? ለኢብራሂምም ቤተሰቦች መጽሐፍንና ጥበብን በእርግጥ ሰጠን። ታላቅንም ንግስናን ሰጠናቸው። ከነሱም (ከአይሁዶች) መካከል በእርሱ (በነብዩ ሙሐመድ ሙሐመድ) ያመነ ክፍል አለ። ከእነርሱም ከዚህ እምነት ያፈገፈገ አለ። አቃጣይነት በገሀነም በቃ።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِنَا سَوۡفَ نُصۡلِيهِمۡ نَارٗا كُلَّمَا نَضِجَتۡ جُلُودُهُم بَدَّلۡنَٰهُمۡ جُلُودًا
غَيۡرَهَا لِيَذُوقُواْ ٱلۡعَذَابَۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَزِيزًا حَكِيمٗا ٥٦ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ
ٱلصَّٰلِحَٰتِ سَنُدۡخِلُهُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ
لَّهُمۡ فِيهَآ أَزۡوَٰجٞ مُّطَهَّرَةٞۖ وَنُدۡخِلُهُمۡ ظِلّٗا ظَلِيلًا ٥٧

**56-57.** እነዚያ በተዐምራታችን የካዱት ሰዎች በእርግጥ እሳትን እናስገባቸዋለን። ስቃይን እንዲቀምሱም ቆዳዎቻቸው በተቃጠሉ ቁጥር ሌሎችን ቆዳዎች እንለውጥላቸዋለን። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነው ነውና። እነዚያ በአላህ አንድነት ያመኑና መልካም ስራዎችን የሰሩ ከስራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች ዘላለም በውስጣቸው ዘወታሪዎች ሲሆኑ በእርግጥ እናስገባቸዋለን። ለእነርሱ በውስጧ ንፁህ ሚስቶች አሏቸው። ወደ አጥላይም ጥላ እናስገባቸዋለን።*

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል: . «በጀነት ውስጥ አንድ በጣም ትልቅና ግዙፍ የሆነ ዛፍ አለ። አንድ ፈረሰ ጋላቢ በእርሱ ጥላ ስር ለአንድ መቶ አመታት ቢጓዝ፤ ፈፅሞ ሊያቋርጠው አይችልም።»

۞ إِنَّ ٱللَّهَ يَأۡمُرُكُمۡ أَن تُؤَدُّواْ ٱلۡأَمَٰنَٰتِ إِلَىٰٓ أَهۡلِهَا وَإِذَا حَكَمۡتُم بَيۡنَ ٱلنَّاسِ أَن تَحۡكُمُواْ بِٱلۡعَدۡلِۚ إِنَّ ٱللَّهَ نِعِمَّا يَعِظُكُم بِهِۦٓۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ سَمِيعَۢا بَصِيرٗا ٥٨ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَأُوْلِي ٱلۡأَمۡرِ مِنكُمۡۖ فَإِن تَنَٰزَعۡتُمۡ فِي شَيۡءٖ فَرُدُّوهُ إِلَى ٱللَّهِ وَٱلرَّسُولِ إِن كُنتُمۡ تُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ وَأَحۡسَنُ تَأۡوِيلًا ٥٩

**58-59.** አላህ አደራዎችን ወደ ባለቤቶቻቸው እንድታደርሱና በሰዎች መካከል በፈረዳችሁ ጊዜም በትክክል እንድትፈርዱ ያዛችኋል። አላህ በእርሱ የሚገስፃችሁ ነገር ምን ያምር ነው። አላህ ሰሚ እና ተመልካች ነውና። እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ተገዙ። መልዕክተኛውን እና ከናንተም የስልጣን ባለቤቶችን ታዘዙ። በማንኛውም ነገር ብትከራከሩ በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ ከሆናችሁ የተከራከራችሁበትን ነገር ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው መልሱት። ይህ የተሻለ እና መጨረሻውም ያማረ ነው።

ከሴቶች ምዕራፍ (58) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ መካን በተቆጣጠሩበት ዕለት የካዕባን ቁልፍ ይዞ የነበረው ዑስማን ቢን ጠልሀ ቁልፉን እንደያዘ ካዕባ ጣሪያ ላይ ወጣና ለነብዩ ቁልፉን አልሰጥም በማለት ከለከለ። ከዚያም አሊይ ቢን አቡጣሊብ ወደ ጣሪያው በመውጣት አስገድደው ተቀበሉት። ይህን ጊዜ ነብዩ ወደ ካዕባ ገብተው ሰግደው ሲወጡ እነዚህ የቁርኣን አናቅፅ ወረዱ። ነብዩ ለአሊይ ቢን አቡጣሊብ «ሄደህ ይቅርታ ጠይቀውና ቁልፉን መልስለት» አሉት። አሊይም ሄደው ቁልፉን ሲመልሱለት አስገድደህ «ወስደህ ስታበቃ እንደገና ትሰጠናለህ» በማለት በቁጣ ተናገረ። አሊይም በበኩላቸው «አላህ በአንተ ምክንያት የቁርኣን አንቀፅ አውርዷል» አላቸውና አንቀፁን አነበቡለት። ኡስማንም እዚያው ኢስላምን ተቀበሉ። በደስታም ተዋጠ። ነብዩም«እስከመጨረሻ ድረስ ውሰዳት። ይህችን ቁልፍ ከአንተ የሚወስዳት ግፈኛ ነው አሉ» እነሆ እስከ ዛሬም ድረስ በዚሁ ሰውዬ ዘሮች እጅ ነው ቁልፉ የሚገኘው። (ዋሒዲ እና ሲዩጢ)

ከሴቶች ምዕራፍ (59) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አብደላህ ኢብኑ ሁዛፋህ የተባለውን ሶሀቢይ መሪ አድርገው ልከውት ሳለ በመንገድ ላይ ተናዶ እሳት «በማንደድ «በዚህ እሳት ውስጥ ግቡ» በማለት ሲያዛቸው ከፊሎቹ እምቢ ሲሉ ከፊሎቹ ደግሞ ትዕዛዙን ለማክበር አስበው ነበር። ይህ ክስተት ለነብዩ (ﷺ) ሲነገራቸው ለሁልጊዜው መመሪያ የሆነው ይህንን ቁርአናዊ አንቀፅ አወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ يَزْعُمُونَ أَنَّهُمْ ءَامَنُوا۟ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْكَ وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبْلِكَ يُرِيدُونَ أَن يَتَحَاكَمُوٓا۟ إِلَى ٱلطَّٰغُوتِ وَقَدْ أُمِرُوٓا۟ أَن يَكْفُرُوا۟ بِهِۦ وَيُرِيدُ ٱلشَّيْطَٰنُ أَن يُضِلَّهُمْ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا ﴿٦٠﴾ وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا۟ إِلَىٰ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ وَإِلَى ٱلرَّسُولِ رَأَيْتَ ٱلْمُنَٰفِقِينَ يَصُدُّونَ عَنكَ صُدُودًا ﴿٦١﴾ فَكَيْفَ إِذَآ أَصَٰبَتْهُم مُّصِيبَةٌۢ بِمَا قَدَّمَتْ أَيْدِيهِمْ ثُمَّ جَآءُوكَ يَحْلِفُونَ بِٱللَّهِ إِنْ أَرَدْنَآ إِلَّآ إِحْسَٰنًا وَتَوْفِيقًا ﴿٦٢﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ يَعْلَمُ ٱللَّهُ مَا فِى قُلُوبِهِمْ فَأَعْرِضْ عَنْهُمْ وَعِظْهُمْ وَقُل لَّهُمْ فِىٓ أَنفُسِهِمْ قَوْلًۢا بَلِيغًا ﴿٦٣﴾

**60-63.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ በአንተ ላይ በተወረደውና ከአንተ በፊትም በተወረደው አምነናል ወደ ሚሉት ሰዎች አላየህምን? በእርሱ እንዲክዱ በእርግጥ የታዘዙ ሲሆኑ ወደ ጣኦት መፋረድን ይፈልጋሉ። ሰይጣንም ከእውነት የራቀን መሳሳት ሊያሳስታቸው ይፈልጋል። ለእነርሱም፡- አላህ ወደ አወረደው ቁርአንና ወደ መልዕክተኛው ኑ በተባሉ ጊዜ መናፍቃንን ከአንተ በሀይል ሲሸሹ ታያቸዋለህ። እጆቻቸውም ባስቀደሙት ጥፋት ምክንያት መከራ በደረሰባቸውና ከዚያ ደግን ሀሳብና ማስማማትን እንጂ ሌላን አልሻትንም በማለት በአላህ የሚምሉ ሆነው ወደ አንተ በመጡ ጌዜ እንዴት ይሆናሉ? እነዚያ አላህ በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅባቸው ናቸው። ከእነርሱ ራስህን አግልል። ገስፃቸውም። ለእነርሱም በነፍሶቻቸው ውስጥ ጠልቆ የመግባት ስሜት ያለውን ቃል ተናገራቸው።*

*✷ ጣጉት የሚለው ቃል «ጡግያን» ወሰንን ማለፍ ከሚለው የአረብኛ ቃል የተወሰደ ነው። ትርጉሙም ወሰንን መጣስ፤ ድንበር ማለፍ፤ በህግ አለመገዛት ማለት ነው። ነብዩ እንዲህ ብለዋል። ሰዎች አላህ ካወረደው ውጪ በሆነ ህግ ከተዳኙ አላህ በእነርሱ ላይ ችግርን በማውረድ ይቀጣቸዋል። ዐብዱላህ ኢብኑ ዐምር ኢብኑ ዓስ እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ዝንባሌያችሁ እኔ የመጣሁበትን መንገድ እስካልተከተለ ድረስ እምነት የላችሁም»። (በተጣራ ሰነድ በኪታቡል ሁጃ የተጠቀሰ ሶሂህ ሐዲስ)*

وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا لِيُطَاعَ بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ وَلَوْ أَنَّهُمْ إِذ ظَّلَمُوٓا۟ أَنفُسَهُمْ جَآءُوكَ فَٱسْتَغْفَرُوا۟ ٱللَّهَ وَٱسْتَغْفَرَ لَهُمُ ٱلرَّسُولُ لَوَجَدُوا۟ ٱللَّهَ تَوَّابًا رَّحِيمًا ﴿٦٤﴾

**64.** ማንንም መልዕክተኛ በአላህ ፈቃድ ሰዎች ሊታዘዙት እንጂ አልላክንም። እነርሱም ነፍሶቻቸውን በበደሉ ጊዜ ወደ አንተ በመጡና አላህን ምህረት በለመኑ መልዕክተኛውም ለእነርሱ ምህረትን በለመነላቸው ኖሮ አላህን ፀፀትን ተቀባይና አዛኝ ሆኖ ባገኙት ነበር።

فَلَا وَرَبِّكَ لَا يُؤۡمِنُونَ حَتَّىٰ يُحَكِّمُوكَ فِيمَا شَجَرَ بَيۡنَهُمۡ ثُمَّ لَا يَجِدُواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَرَجٗا مِّمَّا قَضَيۡتَ وَيُسَلِّمُواْ تَسۡلِيمٗا ٦٥ وَلَوۡ أَنَّا كَتَبۡنَا عَلَيۡهِمۡ أَنِ ٱقۡتُلُوٓاْ أَنفُسَكُمۡ أَوِ ٱخۡرُجُواْ مِن دِيَٰرِكُم مَّا فَعَلُوهُ إِلَّا قَلِيلٞ مِّنۡهُمۡۖ وَلَوۡ أَنَّهُمۡ فَعَلُواْ مَا يُوعَظُونَ بِهِۦ لَكَانَ خَيۡرٗا لَّهُمۡ وَأَشَدَّ تَثۡبِيتٗا ٦٦ وَإِذٗا لَّأٓتَيۡنَٰهُم مِّن لَّدُنَّآ أَجۡرًا عَظِيمٗا ٦٧ وَلَهَدَيۡنَٰهُمۡ صِرَٰطٗا مُّسۡتَقِيمٗا ٦٨

**65-68.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጉዳዩ እነርሱ እንዳሉት አይደለም በጌታህ እምላለሁ በመካከላቸው በተከራከሩበት ፍርድ እስከያስፈርዱህ ከዚያ ከፈረድከው ነገር በነፍሶቻቸው ውስጥ ጭንቀትን እስከማያገኙና ፍፁም መታዘዝን እስከሚታዘዙ ድረስ ትክክለኛ አማኝ አይሆኑም። እኛም በእነርሱ ላይ፡- ነፍሶቻችሁን ግደሉ ወይም ከአገሮቻችሁ ውጡ ማለትን በፃፍን ኖሮ ከእነርሱ ጥቂቶቹ እንጂ ባልሰሩት (ባልተገበሩት) ነበር። እነርሱም በርሱ የሚገሰጹበትንነገር በሰሩ ኖሮ ለእነርሱ መልካምና በእምነታቸው ላይ ለመርጋትም በጣም የበረቱ በሆኑ ነበር። ያን ጊዜ ደግሞ ከእኛ ዘንድ ታላቅን ምንዳ በሰጠናቸው ነበር። ቀጥተኛውንም መንገድ በእርግጥ በመራናቸው ነበር።

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (60-68) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አንድ ቢሸር የተባለ አስመሳይ እና አንድ አይሁድ በአንድ ጉዳይ ተጣልተው ሲጨቃጨቁ ቆዩና አይሁዱ ፍርድ ለማግኘት ወደ ነብዩ እንሂድ ሲል አስመሳዮ ደግሞ የለም ወደ ካዕብ ቢን አሽረፍ (አይሁድ ዓሊም) እንሂድ በማለቱ ክርክር ገጠሙ። ሆኖም አይሁዱ አሸነፈና ለፍርድ ወደ ነብዩ መጡ። እሳቸውም ጉዳዩን ተመልክተው ለአይሁዱ ፈረዱለት። በሙናፊቁ ላይ ፈረዱበት። ሙናፊቁም የነብዩን (ﷺ) ፍርድ ባለመቀበል ወደ ኡመር ሄደው እንዲዳኙት ጠየቀ። ኡመርም የጉዳዩን ዝርዝር ከአይሁዱ ካዳመጡ በኋላ ለሙናፊቁ የነብዩን ፍርድ ያለመቀበሉን ጠየቁትና ያለመቀበሉን አረጋገጡ። ኡመርም ቆየኝ ጠብቀኝ አሉና ወደ ጓዳ ገብተው ሰይፋቸውን ይዘው በመውጣት የሙናፊቁን አንገት በመቁረጥ «የአላህን መልዕክተኛ ውሳኔ ያልተቀበለ የውሸት አማኝን (አስመሳዮችን) አንገት እንዲህ ነው የምቆርጠው» ብለው ሲናገሩ የእርሳቸውን ተግባር በማረጋገጥ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ)

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (34-65) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ወንዶች ሴቶችን የማስተዳደር የመምራት ብቃትና ችሎታ ያላቸው በመሆኑ የቤተሰብ ኃላፊ እንደሆኑ፤
2. መልካም ሴቶችን በአክብሮት መያዝና መንከባከብ በወንዶች ላይ የተጣለ ግዴታ መሆኑንና ተገቢ መሆኑን፤

3. የሚስት ባህርይ አመፀኝነት ሲታይበትና የሥነ. ስርዓት ጉድለት ሲከሰት ይህን የሥነ. ስርዓት ጉድለት ለማረም የሚያስችሉ ሰላማዊ መፍትሄዎች እንዳሉና መፍትሄዎችም ምን እንደሚመስል፤
4. ሴቶችን ሆን ብሎ ለመጎዳት ልዩ ልዩ ምክንያቶች መፍጠር ተገቢ ያልሆነ ባህሪይ መሆኑን፤
5. በባልና ሚስት መሀከል የሚፈጠሩ ቅራኔዎችና አለመግባባቶች ለመፍታት ሽምግልና ጠቃሚ መፍትሄ እንደሆነና አስታራቂ ሽማግሌዎች በጉዳዩ ላይ እንዲገቡ ማድረግ እንደሚገባ፤
6. ኩራት የተወገዘና የተጠላ ብልሹ ምግባር ሲሆን፤ እውቀት ለማካፈል ባለመፈለግ እውቀት መንፈግና መስገብገብም የተከለከለ ነው። በተለይ ኩራት ተገቢነቱ ለአላህ ብቻ በመሆኑ የአላህን ድርሻ የመጋፋት ስራ ነው። በሌላ በኩል መልካም ስራዎችን ለይዩልኝ ብሎ መስራት ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን ከመሆኑም ባሻገር የተከለከለና ለአላህ ተብሎ መተግበር የነበረበትን ሥራ ለሰው ብሎ መስራት ለኪሳራ ይዳረጋል። መጥፎ ጓደኛ መያዝ የተከለከለ መሆኑን አላህ በእነዚህ አናቅፅ ያስተምራል።
7. መጥፎ ጓደኞች የምድራዊና የአኼራዊ ሕይወትን የሚያበላሹ ከመጥፎ ባህሪያት ጋር የሚያዛምዱ በመሆናቸው አደገኛነታቸውን ማወቅ እንደሚገባ።
8. ቀደምት ምሁራን «ዘራ» ማለት የጎመንዘር ፍሬ ወይም የአቧራ ብናኝ ማለት ነው ይሉ ነበር። ይህ የሆነውም በእነሱ ጊዜ የነበረ አነስተኛ ይመስል የነበረው በእነዚህ ነገሮች ስለነበረ ነው። አሁን ግን ብዙ ጥቃቅን ነገሮች ተገኝተዋል። በጣም ዘመናዊ በሆኑ ማጉሊያዎች እንኳን መታየት ያልቻሉና መኖራቸው ግን የተረጋገጠ ብዙ ነገሮች አሉ።
9. አላህ ፍትሀዊ የሆነ ፍትህን አስፋኝ ሙሉ ጌታ መሆኑን፤
10. የትንሳኤ (የቂያማ) ዕለት ሰቆቃና ስቃይ እጅግ ከባድ መከራው የከፋ መሆኑን፤
11. ነብዩ የተሟላ ስብዕና ላቅ ያለ ማዕረግና ክብር ያላቸው ነብይ እንደነበሩ፤
12. ከትዳር ጓደኛ ጋር ወሲባዊ ግንኙነት ከተፈፀመ በኋላ ትጥበት ሳያደርጉ (ሙሉ ገላን ሳይታጠቡ) በመስጂድ ውስጥ መገኘት የተከለከለ እንደሆነና የጀናባ ትጥበት (ከወሲባዊ ግንኙነትና የዘር ፈሳሽ ከወጣ በኋላ የሚደረግ ትጥበት) ግዴታ መሆኑን፤
13. የአላህ ምህረት እጅግ ሰፊ እዝነቱም በዚያው ልክ መሆኑን እንማራለን።
14. አይሁዶች ለሙስሊሞች ያላቸው ጥላቻ የከፋ ሴራቸውም የረቀቀ መሆኑን፤
15. አላህ ለሙዕሚኖች (ለምዕመናን) ብቸኛ መመኪያቸው ስለመሆኑ፤
16. ለነብዩ (ﷺ) ባላቸው አመለካከት በጥላቻ የተሞላ መጥፎ እንደነበር፤
17. ከልብ ውስጥ ሰርፆ የገባ መሰረት የሌለው እምነት ምንም ጥቅም የሌለው መሆኑን፤ «እነሆ! በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በእርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዩችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም» (የመዕዳ፡ **72**) «ባጋሩም ኖሮ ይሰሩት የነበሩት መልካም ተግባር ሁሉ ከእነርሱ በታሰበ ነበር።» (አል. -አንዓም፡ **88**)

   «ብታጋሩ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል። በእርግጥም ከከሓዲያን ትሆናለህ ማለት ወደ አንተም ወደ እነዚያም ካንተ በፊት ወደ ነበሩት በእርግጥ ተወርዷል።» (አዝ-ዙመር፡ **65**)
18. የአላህ ሒዳያ ካልታከለበት በስተቀር የሰው ልጅ እውቀት ብቻውን ወደ ቀናው ጎዳና ለመግባት እንዲችል አስተዋፅኦ አያበረክትም።
19. ሽርክ እጅግ አስከፊና አደገኛ ወንጀል እንደሆነና የሺርክ ኃጢአት ያለ ተውባህ መፍትሄ የሌለው መሆኑን፤
20. እንዲሁም ከሽርክ በታች ያሉ ወንጀሎችን እየሰራ ሳለ በሞት የተቀደመ ሰው አላህ ከፈለገ ሊምረው ካልፈለገ ሊቀጣው የሚችል መሆኑን በአናቅፅ ግልጿል። ኃጢአትን እርግፍ አድርጎ በመተው ተውበት (ንሰሀ) መግባት ተገቢ በመሆኑም ለንሰሀ መቸኮል እጅግ አስፈላጊ መሆኑን፤

21. ዑመር ኢብኑልኸጧብ «እኔ አማኝ ነኝ ያለ ሰው ከሃዲ ነው። እኔ አዋቂ ነኝ ያለ ሰው መሀይም ነው። እኔ የጀነት ነኝ ያለ ሰው የእሳት ነው ብለዋል» ኢብኑ ከሲር ምክንያቱም ይህ ጉዳይ (ገይብ) አላህ ብቻ የሚያውቀው ሩቅ ስለሆነ ስለሆነ ነው።
22. በኢስላም ሰው ራሱን መካብና ማንገስ እንደሌለበት፤
23. አላህ ፍትሀዊ ጌታ መሆኑን መረዳት እንደሚገባ፤
24. የአይሁድ ተንኮልና ሴራ ምን እንደሚመስል፤
25. በኢስላም በጣኦት መካድ ለተውሒድ መሰረታዊ ክፍሎች ዋነኛው መሆኑን በማወቅ ጣኦታትን መካዱ ግዴታ እንደሆነ፤
26. በኢስላም ምቀኝነትና ንፉግነት (ስስት) የተወገዙ መጥፎ ባህሪያት መሆናቸውን፤
27. አብዛሀኞቹ እያወቁ ኢስላምን አንቀበልም በማለት በክህደት ጎዳና ቢጓዙም ጥቂቶቹ ግን እምነትን ተቀብለው ወደ ሀቁ መስመር እንደተቀላቀሉ፤
28. በኢስላም ክህደት ወንጀል በቂያማ ዕለት ቅጣትን ለመቀበል የሚያበቁ ምክንያቶች እንደሆኑ፤
29. በገሀነም ቅጣትን እንዲቀበሉ የሚፈረድባቸው ሰዎች ቆዳቸው በእሳት ተቀጣጥሎ ባለቀ ቁጥር አዲስ ቆዳ እየተተካላቸው ቅጣታቸውን እንዲቀበሉ፤
30. ትክክለኛ እምነት መልካም ስራዎች የጀነትን ፀጋ ለማግኘት የሚያበቁ የጀነት በር መክፈቻ ምክንያቶች መሆናቸውን፤
31. ጀነት ለትክክኛ አማኞች የተዘጋጀች የደስታ የፍስሀና የተድላ ሀገር መሆኗን፤
32. አማናን (አደራን) ጠብቆ ለባለቤቱ ማስረከብ ከኢስላማዊ ድንጋጌዎች አንዱ መሆኑን።
33. ፍትሀን መጠበቅና በዕለት ተዕለት የኑሮ ሂደት ውስጥ የሚያጋጥሙ ጉዳዩችን በፍትሀዊነት ማስተናገድ ግዴታ መሆኑን።
34. አላህንና ነብዩ እንዲሁም የሙስሊም አስተዳዳሪዎች፤ ኡለማዎችን መታዘዝ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
35. ቁርኣንና ሀዲስን መሰረት አድርጎ ብይን መስጠት የሚችል አዋቂ እያለ በሰው ሰራሽ ሕግጋት ለመዳኘት መፈለግ የተከለከለ መሆኑን፤
36. ከመሃይማን ጋር መነታረክ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ የሚያመዝን በመሆኑ አላዋቂዎችን ችላ ማለት ተገቢ እንደሆነ፤
37. በመንፈሳዊ እምነታዊ፤ አምልኮታዊ፤ ማህበራዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ የተከራከሩ ሰዎች ለክርክራቸው ብቸኛ አስታራቂ ሀሳብ ለማግኘት ይችሉ ዘንድ ዳኝነቱን ለቁርኣንና ሀዲስ መተው ይገባቸዋል። በአለማችን ህ ሰብ ግላዊ፤ ቤተሰባዊ፤ ማህበራዊና አለም አቀፍ ችግሮች ሁሉ መፍትሄው ወደ ቁርኣንና ሀዲስ መመለስ ብቻ መሆኑን፤
38. አላህንና ነብዩ በፍፁም ፈቃደኝነት መታዘዝና የአላህን ውሳኔ መቀበል ግዴታ ነው። እንዲሁም ከቁርኣንና ከሃዲስ ውጭ ፍትሀን ለመፈለግ መሞከር የተከለከለ ስለመሆኑ ከአናቅፅ እንማራለን።

وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلَّذِينَ أَنْعَمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ
وَٱلصِّدِّيقِينَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَٱلصَّٰلِحِينَۚ وَحَسُنَ أُوْلَٰٓئِكَ رَفِيقًا ﴿٦٩﴾
ذَٰلِكَ ٱلْفَضْلُ مِنَ ٱللَّهِۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ عَلِيمًا ﴿٧٠﴾

**69-70.** አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ሁሉ እነዚያ ከእነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ከለገሳቸው ከነብያት፤ ከፃድቃን፤ ከሰማዕታትና ከመልካሞቹ ጋር ይሆናሉ። የእነዚያም ጓደኝነት አማረ። ይህ ችሮታ ከአላህ የተለገሰ ነው። አዋቂነትም በአላህ በቃ።

ከሴቶች ምዕራፍ (69) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰውባን የተባለ አንድ የነብዩ ሰራተኛ ነበር። በጣም ይወዳቸው ነበር። እናም ከዕለታት አንድ ቀን በጣም ከስቶና ሰውነቱ ተጎሳቁሎ ስለአዩት «ሰውባን ሆይ! ምን ሆነህ ነው እንዲህ የተጎሳቀልከው» በማለት ሲጠይቁት ሰውባንም የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርቦኝ ጠምቶኝ ወይም አሞኝ አይደለም። እርሶዎን ስለምወድና ስለምናፍቅ ብቻ ነው። በተለይም የአኼራን ሁኔታ ሳስታውስ ጀነት ያለ መግባቴን የእርሶዎን ጀነት መግባት ብሎም ጀነት እንኳን ብገባ ከእርስዎ ጋር ያለኝን የደረጃ መራራቅ ሳስታውስ ነው» ሲላቸው ነብዩ (ﷺ) ዝም ብለው ምንም አይነት መልስ ሳይሰጡ ባሉበት ይህ አንቀፅ ወረደና የሰውየውን ጥያቄና ፍላጎት መልስ ሰጠ። (ዋሒዲ፤ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ خُذُواْ حِذْرَكُمْ فَٱنفِرُواْ ثُبَاتٍ أَوِ ٱنفِرُواْ جَمِيعًا ﴿٧١﴾
وَإِنَّ مِنكُمْ لَمَن لَّيُبَطِّئَنَّ فَإِنْ أَصَـٰبَتْكُم مُّصِيبَةٌ قَالَ قَدْ أَنْعَمَ ٱللَّهُ عَلَىَّ إِذْ لَمْ
أَكُن مَّعَهُمْ شَهِيدًا ﴿٧٢﴾ وَلَئِنْ أَصَـٰبَكُمْ فَضْلٌ مِّنَ ٱللَّهِ لَيَقُولَنَّ كَأَن لَّمْ تَكُنۢ
بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُۥ مَوَدَّةٌ يَـٰلَيْتَنِى كُنتُ مَعَهُمْ فَأَفُوزَ فَوْزًا عَظِيمًا ﴿٧٣﴾

**71-73.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ጥንቃቄያችሁን ያዙ። ክፍልፍልም ወይም በአንድ ሆናችሁ ለዘመቻ ውጡ። ከናንተ ውስጥ በእርግጥ ከዘመቻ ወደ ኋላ የሚንጓደድ ሰው አለ። አደጋም ካገኛችሁ ከእነርሱ ጋር ባለመሆኔ አላህ በእኔ ላይ በእርግጥ ፀጋዬን ለገሰልኝ ይላል። ከአላህ የሆነ ችሮታ ካገኛችሁ ደግሞ በእናንተና በእነርሱ መካከል ፍቅር እንዳልነበረ ሁሉ ታላቅ እድል አገኘ ዘንድ ከእነርሱም ጋር ምን ነው በሆንኩ ወይ ምኞቴ! ይላል።

۞ فَلْيُقَـٰتِلْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ٱلَّذِينَ يَشْرُونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا بِٱلْـَٔاخِرَةِ
وَمَن يُقَـٰتِلْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ فَيُقْتَلْ أَوْ يَغْلِبْ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا ﴿٧٤﴾

**74.** እናም እነዚያ ቅርቧን ህይወት በመጨረሻይቱ ሕይወት የሚለውጡ (የሚገዙ) ክፍሎች በአላህ መንገድ ይጋደሉ። በአላህ መንገድ የሚጋደልና ከዚያ የሚገደልም ወይም የሚያሸንፍ ሰው ታላቅ ምንዳን በእርግጥ እንሰጠዋለን።

وَمَا لَكُمْ لَا تُقَٰتِلُونَ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱلْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ ٱلرِّجَالِ وَٱلنِّسَآءِ وَٱلْوِلْدَٰنِ ٱلَّذِينَ
يَقُولُونَ رَبَّنَآ أَخْرِجْنَا مِنْ هَٰذِهِ ٱلْقَرْيَةِ ٱلظَّالِمِ أَهْلُهَا وَٱجْعَل لَّنَا مِن لَّدُنكَ وَلِيًّا وَٱجْعَل
لَّنَا مِن لَّدُنكَ نَصِيرًا ﴿٧٥﴾ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ يُقَٰتِلُونَ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ يُقَٰتِلُونَ فِى
سَبِيلِ ٱلطَّٰغُوتِ فَقَٰتِلُوٓا۟ أَوْلِيَآءَ ٱلشَّيْطَٰنِ ۖ إِنَّ كَيْدَ ٱلشَّيْطَٰنِ كَانَ ضَعِيفًا ﴿٧٦﴾

75-76. (አማኞች ሆይ!) በአላህ መንገድና ከወንዶች ከሴቶችና ከልጆችም የሆኑትን እነዚያን፡- ጌታችን ሆይ! ከዚህች ባለቤቶቿ በዳይ ከሆኑባት ከተማ አውጣን፤ ከአንተም ዘንድ ለእኛ አሳዳሪን አድርግልን፤ ከአንተ ዘንድም ለእኛ ረዳትን አድርግልን የሚሉትን ደካሞች ሰዎች ለማዳን የማትዋጉት ለምንድ ነው? እነዚያ በትክክል ያመኑት ሰዎች በአላህ መንገድ ይዋጋሉ። እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ደግሞ በጣኦት መንገድ ይዋጋሉ። እናም (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) የሰይጣን ቡድኖችን ተዋጉ። የሰይጣን ተንኮል ደካማ ነውና።

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ قِيلَ لَهُمْ كُفُّوٓا۟ أَيْدِيَكُمْ وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُوا۟ ٱلزَّكَوٰةَ فَلَمَّا كُتِبَ
عَلَيْهِمُ ٱلْقِتَالُ إِذَا فَرِيقٌ مِّنْهُمْ يَخْشَوْنَ ٱلنَّاسَ كَخَشْيَةِ ٱللَّهِ أَوْ أَشَدَّ خَشْيَةً ۚ وَقَالُوا۟ رَبَّنَا
لِمَ كَتَبْتَ عَلَيْنَا ٱلْقِتَالَ لَوْلَآ أَخَّرْتَنَآ إِلَىٰٓ أَجَلٍ قَرِيبٍ ۗ قُلْ مَتَٰعُ ٱلدُّنْيَا قَلِيلٌ وَٱلْءَاخِرَةُ خَيْرٌ
لِّمَنِ ٱتَّقَىٰ وَلَا تُظْلَمُونَ فَتِيلًا ﴿٧٧﴾

77. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ ለእነርሱ፡- እጆቻችሁን ከመጋደል ሰብስቡ፤ ሶላትን ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፤ ግዴታ ምፅዋትም ስጡ። ወደ ተባሉት አላየህምን? በእነርሱ ላይ መጋደል ግዴታ በሆነባቸው ጊዜ ደግሞ ከእነርሱ መካከል ከፊሎቹ ወዲያውኑ ሰዎችን ልክ አላህን እንደሚፈሩ ወይም የበለጠ ይፈራሉ። ጌታችን ሆይ! በእኛ ላይ መጋደልን ለምን ደነገግህ? እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አታቆየንም ኖሯልን? ይላሉ። የቅርቢቱ ሕይወት ጥቅም አነስተኛ ነው። የመጨረሻይቱ ዓለም ጥቅም ግን አላህን ለሚፈራ ሰው ሁሉ በላጭ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፣ በተምር ፍሬ ውስጥ ያለችን ክር ያህል እንኳ አትበደሉም በላቸው።

ከሴቶች ምዕራፍ (77) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ቀደምት ሙስሊሞች ማለት ዐብዱረህማን ቢን አውፍ፤ ሚቅዳድ ቢን አስወድ፤ ቁዳመህ ቢንመዝዑን፤ ሰዕድ ቢን አቡወቃስና ሌሎችም ከመካ ከሐዲያን በኩል ከመጠን በላይ ስቃይና ጉዳት ይደርስባቸው ነበርና አንዳንዶቹ ለነብዩ (ﷺ) «ፈቃድ ይስጡን እነዚህን ሰዎች እንዋጋቸው በማለት በተደጋጋሚ ጠይቋቸው ነብዩ (ﷺ) ግን «አልታዘዝኩምና ተቆጠቡ ሲሏቸው ኖረው ወደ መዲና ከተሰደዱ በኋላ ጂሃድ ሲታዘዙ አንዳንዶች ስለ ከበዳቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَيْنَمَا تَكُونُواْ يُدْرِككُّمُ ٱلْمَوْتُ وَلَوْ كُنتُمْ فِى بُرُوجٍ مُّشَيَّدَةٍۗ وَإِن تُصِبْهُمْ حَسَنَةٌ يَقُولُواْ هَٰذِهِۦ مِنْ عِندِ ٱللَّهِۖ وَإِن تُصِبْهُمْ سَيِّئَةٌ يَقُولُواْ هَٰذِهِۦ مِنْ عِندِكَۚ قُلْ كُلٌّ مِّنْ عِندِ ٱللَّهِۖ فَمَالِ هَٰٓؤُلَآءِ ٱلْقَوْمِ لَا يَكَادُونَ يَفْقَهُونَ حَدِيثًا ﴿٧٨﴾

78. የትም ስፍራ ብትሆኑ እንኳን ሞት ያገኛችኋል፡፡ በጠነከሩ ህንፃዎች ውስጥም ብትሆኑም እንኳን፡፡ ደግ ነገር ካገኛቸው ይህ ከአላህ ዘንድ የመጣ ነው ይላሉ፡፡ መከራ ካገኛቸው ግን ይህ ከአንተ ዘንድ የመጣ ነው ይላሉ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁሉም (ደጉም ክፉውም) ከአላህ ዘንድ የመጣ ነው በላቸው፡፡ እነዚህ ሰዎች ንግግርን ሊረዱ የማይቀርቡት ለምንድ ነው?

ከሴቶች ምዕራፍ (78) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በኡሁድ ጦርነት ዕለት የሞቱትን ሙስሊሞች ከማመስገን ይልቅ ከዘመዶቻቸው ዘንድ ቀርተው የነበሩ አስመሳዮች ከእኛ ጋር ቀርተው ቢሆን ኖሮ አይሞቱም ነበር» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ዋሒዲ፤ ኢብኑል ጀውዚ እና ቁርጡቢ)

مَّآ أَصَابَكَ مِنْ حَسَنَةٍ فَمِنَ ٱللَّهِۖ وَمَآ أَصَابَكَ مِن سَيِّئَةٍ فَمِن نَّفْسِكَۚ وَأَرْسَلْنَٰكَ لِلنَّاسِ رَسُولًاۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدًا ﴿٧٩﴾ مَّن يُطِعِ ٱلرَّسُولَ فَقَدْ أَطَاعَ ٱللَّهَۖ وَمَن تَوَلَّىٰ فَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ عَلَيْهِمْ حَفِيظًا ﴿٨٠﴾

79-80. (የሰው ልጅ ሆይ፣) ደግ ነገር የሚያገኝህ ከአላህ ችሮታ ነው፡፡ የሚደርስብህ መከራ ግን ከራስህ ጥፋት የተነሳ ነው፡፡ ለሰዎች ሁሉ መልዕክተኛ አድርገን ላክንህ፡፡ መስካሪነትም በአላህ በቃ፡፡ መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ሁሉ በእርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡ ከትዕዛዝም የሸሸ ሰው ጉዳይ አያሳስብህ፡፡ በእነርሱ ላይ ጠባቂ አድርገን አላክንህምና፡፡

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (66-79) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎች፡-**

1. አላህ ባሪያዎቹን ለመፈተን በውስብስብ ነገሮች እንደሚሞክራቸውና እምነት ሊጨምርና ሊቀንስ የሚችል መሆኑን፤
2. አላህንና ነብዩን (ﷺ) መታዘዝ የነብያትን የሰማዕታትን የመልካም ሰዎችንና የእውነተኞችን ጓደኝነት የሚያስገኝ መሆኑን፤
3. ሙስሊሞች ለጦርነትም ሆነ ለሰላም እራሳቸውን አዘጋጅተው ሊጠብቁ እንደሚገባ፤
4. የሙስሊሙ ኃይል ወታደራዊ ብቃቱ የሚያስተማምን የተሟላ አመራር ያለው ጦር ሰራዊት ሊኖረው የሚገደድ መሆኑን፤
5. ከሙስሊሞችም የሙስሊሙን እንቅስቃሴ ወደ ኋላ የሚጎትቱ ስለሚኖሩ ለእነዚህ ሰዎች ጆሮ መስጠት እንደማያስፈልግ፤

6. የተጨቆኑ ሙስሊሞችን ህልውና ለመታደግ ሲባል ጦርነት መውጣት ግዴታ መሆኑን፤
7. ለአላህ ሃይማኖት የበላይነት ሲል ጂሃድ የወጣ ሙስሊም ይህችን ጠፊ ዓለም በአኼራ የለወጠ ብልህ ሰው መሆኑን፤
8. ሙጃሂድ በጦርነቱ ሂደት ድልን ቢያገኝም ሆነ ሽንፈትን ቢቀምስ የሚያገኘው ምንዳ ትልቅ መሆኑን፤
9. ሙዕሚኖች ጠላቶቻቸውን በመፍራት ከጂሃድ ሊሸሹና ጂሃድን ሊተው እንደማይገባ፤
10. ችኩልነትና ፍርሃት በኢስላም የተወገዙ መሆናቸውን፤
11. ከሞት በኋላ ያለውን የአኼራ ሕይወት አለማዊና ከዱንያ (ከምድራዊ ዓለም) በላጭ መሆኗን መረዳት እንደሚገባ፤
12. ሞት ፍጡራን ሁሉ የሚቀምሱት፤ ማንም ሊያመልጠው የማይችል የማይቀር ክስተት መሆኑን፤
13. ጥሩም ሆነ መጥፎ ከአላህ የሚወሰን መሆኑን ማመንና መቀበል እንደሚያስፈልግ መልአክ የሚባሉ ፍጡራን እንዳለና እነሱንም ማሞገስና ማመስገን፤
14. ለዲን ብሎ መሰደድ ያለውን ከፍተኛ ማዕረግ እንማራለን።

وَيَقُولُونَ طَاعَةٌ فَإِذَا بَرَزُواْ مِنْ عِندِكَ بَيَّتَ طَآئِفَةٌ مِّنْهُمْ غَيْرَ ٱلَّذِى تَقُولُ ۖ
وَٱللَّهُ يَكْتُبُ مَا يُبَيِّتُونَ ۖ فَأَعْرِضْ عَنْهُمْ وَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِ ۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَكِيلًا ﴿٨١﴾

**81.** (መልክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አጠገብህ ሲሆኑ የአንተ ታዛዥ ነን ይላሉ። ከአንተ ዘንድ በወጡ ጊዜ ከእነርሱ ከፊሎቹ ከዚያ በአጠገብህ ከሚሉት ሌላን በልቦቻቸው ያሳድራሉ። አላህ በልቦቻቸው የሚያሳድሩትን ነገር ሁሉ ይፅፋል። ስለዚህ ተዋቸውና በአላህ ላይ ተመካ። መመኪያነት በአላህ በቃ።

أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلْقُرْءَانَ ۚ وَلَوْ كَانَ مِنْ عِندِ غَيْرِ ٱللَّهِ لَوَجَدُواْ فِيهِ ٱخْتِلَٰفًا كَثِيرًا ﴿٨٢﴾

**82.** ቁርአንን አያስተነትኑምን? ከአላህ ያልመጣ በነበረ ኖሮ በውስጡ ብዙ መለያየትን ባገኙ ነበር።

وَإِذَا جَآءَهُمْ أَمْرٌ مِّنَ ٱلْأَمْنِ أَوِ ٱلْخَوْفِ أَذَاعُواْ بِهِۦ ۖ وَلَوْ رَدُّوهُ إِلَى ٱلرَّسُولِ
وَإِلَىٰٓ أُوْلِى ٱلْأَمْرِ مِنْهُمْ لَعَلِمَهُ ٱلَّذِينَ يَسْتَنۢبِطُونَهُۥ مِنْهُمْ ۗ وَلَوْلَا فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ
وَرَحْمَتُهُۥ لَٱتَّبَعْتُمُ ٱلشَّيْطَٰنَ إِلَّا قَلِيلًا ﴿٨٣﴾

**83.** ፀጥታን ወይም ፍርሃት የሚመለከት ወሬ በመጣላቸው ጊዜ እርሱን ያጋንናሉ። ሁሉንም ወደ መልዕክተኛውና ከእነርሱ መካከል የጉዳዩ ባለቤቶች ወደ ሆኑት አዋቂዎቹ በመለሱት ኖሮ እነዚያ ከእነርሱ መካከል ነገሩን በትክክል የሚረዱት ክፍሎች* ባወቁት ነበር። በእናንተ ላይ የአላህን ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከጥቂቶቹ በስተቀር ሰይጣንን በተከተላችሁ ነበር።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም ለእኔ የታዘዘ ሰው በእርግጥ አላህን ታዝዟል። እንዲሁም ማንኛውም ለእኔ የማይታዘዝ ሰው በእርግጥ አላህን አልታዘዘም። ማንኛውም እኔ የመረጥኩትን መሪ የታዘዘ በእርግጥ ለኔ ታዝዟል። እንዲሁም ማንኛውም እኔ የመረጥኩትን መሪ ያልታዘዘ በእርግጥ ለኔ አልታዘዘም»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሁሉም የእኔ ተከታዮች ጀነት ይገባሉ። እምቢኝ ካለ ሰው በስተቀር» ሶሓባዎችም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ማነው እምቢኝ የሚለው?» ብለው ጠየቋቸው። እሳቸውም «ለኔ የታዘዘ ሰው ጀነት ይገባል። ለኔ ያልታዘዘው ሰው ነው ጀነት ለመግባት እምቢኝ ያለው»

ከሴቶች ምዕራፍ (83) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዑመር ኢብኑልኸጧብ «መስጊድ ስገባ ሰዎች አንገታቸውን ደፍተው ጠጠር እያገላበጡ «ነብዩ (ﷺ) ሚስቶቻቸውን ፈቱ» እያሉ አዝነው አየኋቸው። እና ከመስጊዱ በር ላይ በመቆም ድምጼን ከፍ አድርጌ «ሚስቶቻቸውን አልፈቱም ብዬ ስለተናገርኩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው» በማለት ተናግረዋል። (ሙስሊም፤ ጦበሪ እና ዋሒዲ)

فَقَٰتِلۡ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ لَا تُكَلَّفُ إِلَّا نَفۡسَكَۚ وَحَرِّضِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَۖ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَكُفَّ
بَأۡسَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۚ وَٱللَّهُ أَشَدُّ بَأۡسٗا وَأَشَدُّ تَنكِيلٗا ٨٤

**84.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ መንገድ ተዋጋ። ራስህን እንጂ ሌላን አትገደድም። ምዕመናንንም በአላህ መንገድ ላይ በመዋጋት ላይ አደፋፍራቸው። አላህ የእነዚያን የካዱትን ሰዎች ኃይል ሊከለክል ይከጀላል። አላህ በሃይል በመያዙ የበረታና ቅጣቱም የጠነከረ ነው።

مَّن يَشۡفَعۡ شَفَٰعَةً حَسَنَةٗ يَكُن لَّهُۥ نَصِيبٞ مِّنۡهَاۖ وَمَن يَشۡفَعۡ شَفَٰعَةٗ سَيِّئَةٗ يَكُن لَّهُۥ
كِفۡلٞ مِّنۡهَاۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ مُّقِيتٗا ٨٥ وَإِذَا حُيِّيتُم بِتَحِيَّةٖ فَحَيُّواْ بِأَحۡسَنَ مِنۡهَآ
أَوۡ رُدُّوهَآۗ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٍ حَسِيبًا ٨٦ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ لَيَجۡمَعَنَّكُمۡ إِلَىٰ يَوۡمِ
ٱلۡقِيَٰمَةِ لَا رَيۡبَ فِيهِۗ وَمَنۡ أَصۡدَقُ مِنَ ٱللَّهِ حَدِيثٗا ٨٧

**85-87.** መልካም መታደግን የሚታደግ (ሽምግልናን የሚሸመግል) ሰው ለራሱ ከእርሷ እድል ይኖረዋል። መጥፎ መታደግንም የሚታደግ ሰው ለእርሱ ከእርሷ ድርሻ ይኖረዋል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ሰላምታ በቀረበላችሁ ጊዜ ከእርሷ ይበልጥ ባማረ ሰላምታን መልሱ።✷ ወይም እርሷኑ ራሷን መልሷት። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ተቆጣጣሪ ነውና። አላህ ከእርሱ በስተቀር ትክክለኛ አምላክ የለም። ወደ ትንሳኤ ቀን በእርሱ ጥርጥር የሌለበት ሲሆን በእርግጥ ይሰበስባችኋል። በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማን ነው?

✷ ይህን በተመለከተ ሙስሊም በዘገቡት ሃዲሥ ነቢዩ (ሰለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) እንዲህ ብለዋል ጀነት አትገቡም እስካላመናችሁ ድረስ በትክክል አታምኑም እስካልተዋደዳችሁ ድረስ የምትዋደዱበትን ነገር ላመላክታችሁን? ሰላምታን በመካከላችሁ ግልጽ አድርጉ ተለዋወጡ።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (80-86) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋናዋናዎች፡**

1. ነብዩ መታዘዝና አሚን ማለት አላህን እንደመታዘዝ እንደሆነ፤
2. የቁርአንን ውስጠ ሚስጥር መመራመርና አስተንትኖ ማንበብ ግዴታ መሆኑን፤
3. የቁርአን ድንጋጌዎች እርስ በእርሳቸው የማይፋለሱ መሆናቸው፤
4. የጦርነት እስትራቴጂና ምስጢሮች የጦርነቱን የሐይልና የእድል ሚዛን የሚወስኑ ዋነኛ ነጥቦች መሆናቸውን፤
5. አብዛሀኞቹ የሰው ልጆች በሚሰሙት ነገር በመማረክ ተከታይ የመሆን አዝማሚያ እንደሚያሳዩ፤
6. ነብዩ አላማቸውን ከግብ ለማድረስ ወደ ኋላ የማይሉ ደፋርና ጀግና ነብይ እንደነበሩ፤
7. ጦርነት በሙሉ ፍላጎት ሊከወን የሚገባ ጉዳይ በመሆኑ በማስገደድ ሳይሆን በማግባባት መሆኑን፤
8. ስምምነትን ለማስፈንና መልካምነትንም እውን ለማድረግ፤ እርቅን ለማውረድ ሽምግልና የላቀ ሚና እንዳለው፤
9. ሰላም ለሚያቀርብልን ሰው አፀፋውን በተመሳሳይ መልኩ ወይም በበለጠ ሁኔታ መስጠት ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

۞ فَمَا لَكُمْ فِي ٱلْمُنَٰفِقِينَ فِئَتَيْنِ وَٱللَّهُ أَرْكَسَهُم بِمَا كَسَبُوٓا۟ ۚ أَتُرِيدُونَ أَن تَهْدُوا۟ مَنْ
أَضَلَّ ٱللَّهُ ۖ وَمَن يُضْلِلِ ٱللَّهُ فَلَن تَجِدَ لَهُۥ سَبِيلًا ﴿٨٨﴾ وَدُّوا۟ لَوْ تَكْفُرُونَ كَمَا كَفَرُوا۟
فَتَكُونُونَ سَوَآءً ۖ فَلَا تَتَّخِذُوا۟ مِنْهُمْ أَوْلِيَآءَ حَتَّىٰ يُهَاجِرُوا۟ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ ۚ فَإِن تَوَلَّوْا۟
فَخُذُوهُمْ وَٱقْتُلُوهُمْ حَيْثُ وَجَدتُّمُوهُمْ ۖ وَلَا تَتَّخِذُوا۟ مِنْهُمْ وَلِيًّا وَلَا نَصِيرًا ﴿٨٩﴾

**88-89.** (አማኞች ሆይ)፣ በመናፍቃን ጉዳይ አላህ በስራዎቻቸው ምክንያት ወደ ክህደት የመለሳቸው ሲሆኑ እናንተ ለሁለት ቡድን የተከፈላችሁ ምን ሆናችሁ ነው? አላህ ያጠመመውን ሰው ልታቀኑ ታስባላችሁን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ያሳሳተውን ሰው ለእርሱ መንገድንም ፈፅሞ አታገኝለትም። (አማኞች ሆይ)፣ (መናፍቃን በአላህ እንደ ካዱ ሁሉ) እናንተም ብትክዱና ከእነርሱ ጋር እኩል ብትሆኑ ተመኙ። በአላህ መንገድ እስከሚሰደዱ ድረስ ከእነርሱ መካከል ወዳጆችን አትያዙ። ከእምነት ካፈገፈጉ ማርኳቸው። ባገኛችሁት ስፍራ ሁሉ ግደሏቸው። ከእነርሱም ወዳጅንና ረዳትን አትያዙ።

*ከሴቶች (88) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ወደ ኡሁድ ዘመቻ ሲጓዙ የተወሰኑ አስመሳዮች ከጉዞ በመሸሽ ወደ ኋላ ስለቀሩ ሶሃቦች እነዚህን አስመሳዮች በተመለከተ በሁለት ተከፈሉ። አንዱ ቡድን እንምታቸው ሲል ሌላው ደግሞ በፍፁም ለምን እንመታቸዋለን? ሙስሊሞች አይደሉም እንዴ ባይሆን አላህም በጉዳዩ ብይን ለመስጠት ከአያዎቹ ውስጥ የተወሰኑትን አወረደ። በዚህ አጋጣሚ ነበር ነብዩ፡- «እሳት የብረት ቆሻሻን ዝገት ለማፅዳት እንደሚጠቅም ሁሉ መልካምነትም መንፈሳዊ ቆሻሻነትን ለማፅዳት ይጠቅማል» ሲሉ የተናገሩት። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)*

إِلَّا ٱلَّذِينَ يَصِلُونَ إِلَىٰ قَوۡمِۭ بَيۡنَكُمۡ وَبَيۡنَهُم مِّيثَٰقٌ أَوۡ جَآءُوكُمۡ حَصِرَتۡ صُدُورُهُمۡ أَن
يُقَٰتِلُوكُمۡ أَوۡ يُقَٰتِلُواْ قَوۡمَهُمۡۚ وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَسَلَّطَهُمۡ عَلَيۡكُمۡ فَلَقَٰتَلُوكُمۡۚ فَإِنِ ٱعۡتَزَلُوكُمۡ
فَلَمۡ يُقَٰتِلُوكُمۡ وَأَلۡقَوۡاْ إِلَيۡكُمُ ٱلسَّلَمَ فَمَا جَعَلَ ٱللَّهُ لَكُمۡ عَلَيۡهِمۡ سَبِيلٗا ٩٠ سَتَجِدُونَ
ءَاخَرِينَ يُرِيدُونَ أَن يَأۡمَنُوكُمۡ وَيَأۡمَنُواْ قَوۡمَهُمۡ كُلَّ مَا رُدُّوٓاْ إِلَى ٱلۡفِتۡنَةِ أُرۡكِسُواْ فِيهَاۚ
فَإِن لَّمۡ يَعۡتَزِلُوكُمۡ وَيُلۡقُوٓاْ إِلَيۡكُمُ ٱلسَّلَمَ وَيَكُفُّوٓاْ أَيۡدِيَهُمۡ فَخُذُوهُمۡ وَٱقۡتُلُوهُمۡ حَيۡثُ
ثَقِفۡتُمُوهُمۡۚ وَأُوْلَٰٓئِكُمۡ جَعَلۡنَا لَكُمۡ عَلَيۡهِمۡ سُلۡطَٰنٗا مُّبِينٗا ٩١

**90-91.** እነዚያ ከእናተና ከእነርሱ መካከል ቃል ኪዳን ወዳላቸው ህዝቦች የሚጠጉና ወይም እናንተን ለመጋደል ወይም ወገኖቻቸውን ለመጋደል ልቦቻቸው የተጨነቁ ሆነው የመጧችሁ ሲቀሩ (እነዚያንማ አትጋደሏቸው)። አላህ በፈለገ ኖሮ በእናንተ ላይ ሀይል በሰጣቸውና በተዋጓችሁ ነበር። ቢተዋችሁ ባይዋጓችሁና ወደ እናንተ የእርቅን ሀሳብ ቢያቀርቡ አላህ ለእናንተ በእነርሱ ላይ የመዋጋት መንገድን አላደረገም። ከናንተም ሆነ ከወገኖቻቸው ለመዳን የሚፈልጉ ሌሎች ቡድኖች ታገኛላችሁ። ወደ ሁውከት እንዲመለሱ በተጠሩ ቁጥር በእርሷ ውስጥ ይዘፈቃሉ። ባይተዋችሁና እርቅን ካለቀረቡላችሁ እጆቻቸውን ባይሰበስቡ ባገኛችኋቸው ስፍራ ሁሉ ማርኳቸው። ግደሏቸውም። እነዚያንም ለእናንተ በእነርሱ ላይ ግልፅ ማስረጃን አድርገንላችኋል።

*ከሴቶች ምዕራፍ (90) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሱራቃ ኢብኑ ማሊክ ነብዩ (ﷺ) ኻሊድ ኢብኑ ወሊድን ወደ ሱራቃ ቤተሰቦች ማለትም በኒ ሙድሊጅ ወደ ሚባሉት ለመላክ ማሰባቸውን ሲሰማ ወደ ነብዩ መጥቶ ኻሊድን ወደ እኔ ዘመዶች ልታዘምተው ነው መባሉን ሰምቻለሁ። ዘመዶችህ የመካ ሰዎች ከሰለሙ የእኔ ዘመዶችም እንዲሰልሙ ካልሰለሙ ደግሞ በፈለጉት እምነት እንዲቀጥሉ ይሆኑ ዘንድ እንድትርቃቸው ጌታ በሰጠህ ፀጋ እማፀንሀለሁ። ሲላቸው ነብዩ (ﷺ) የኻሊድን እጅ በመያዝ ውሰደውና እሱ ደስ እንዳለው አድርግለት አሉት። ኻሊድም በትዕዛዙ መሰረት በነብዩ ላይ ማንንም እንዳይረዱና ቁረይሾች ከሰለሙ እንዲሰልሙ አስረድተው እርቋቸው መጣ በዚህ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ኢብኑከሲር እና ሱዩጢ)*

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (87-91) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎች፡-**

1. አምልኮት (ዒባዳ) የሚገባው ለአንድ አላህ ብቻ መሆኑን፤
2. ከሞት በኋላ መነሳትና መጠየቅ የማይቀር እውነታ መሆኑን፤
3. ከአስመሳዮች (አስመሳዩች) ጋር እንዴት በጥንቃቄ መኗኗር እንደሚገባን እንማራለን።

وَمَا كَانَ لِمُؤْمِنٍ أَن يَقْتُلَ مُؤْمِنًا إِلَّا خَطَـًٔا ۚ وَمَن قَتَلَ مُؤْمِنًا خَطَـًٔا فَتَحْرِيرُ رَقَبَةٍ مُّؤْمِنَةٍ
وَدِيَةٌ مُّسَلَّمَةٌ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦٓ إِلَّآ أَن يَصَّدَّقُوا۟ ۚ فَإِن كَانَ مِن قَوْمٍ عَدُوٍّ لَّكُمْ وَهُوَ مُؤْمِنٌ
فَتَحْرِيرُ رَقَبَةٍ مُّؤْمِنَةٍ ۖ وَإِن كَانَ مِن قَوْمٍۭ بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُم مِّيثَـٰقٌ فَدِيَةٌ مُّسَلَّمَةٌ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦ
وَتَحْرِيرُ رَقَبَةٍ مُّؤْمِنَةٍ ۖ فَمَن لَّمْ يَجِدْ فَصِيَامُ شَهْرَيْنِ مُتَتَابِعَيْنِ تَوْبَةً مِّنَ ٱللَّهِ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ
عَلِيمًا حَكِيمًا ﴿٩٢﴾ وَمَن يَقْتُلْ مُؤْمِنًا مُّتَعَمِّدًا فَجَزَآؤُهُۥ جَهَنَّمُ خَـٰلِدًا فِيهَا وَغَضِبَ ٱللَّهُ
عَلَيْهِ وَلَعَنَهُۥ وَأَعَدَّ لَهُۥ عَذَابًا عَظِيمًا ﴿٩٣﴾

**92-93.** ትክክለኛ አማኝ በስህተት ካልሆነ በስተቀር አማኝን መግደል አይገባውም። አማኝን በስህተት የገደለ ሰው አማኝ ባሪያን ነፃ ማውጣትና ለቤተሰቦቹ ምህረት ካላደረጉለት በስተቀር የምትሰጥ ጉማ መክፈል አለበት። ተገዳዩ ምዕመን ሲሆን ለእናንተ ጠላት ከሆነ ህዝቦች ጋር ቢሆን አማኝን ባሪያ ነፃ ማውጣት ብቻ አለበት። (ተገዳዩ) ከናንተ እና ከእነርሱ መካከል ቃል ኪዳን ካላቸውም ህዝቦች ጋር ቢሆን ለቤተሰቦቹ የምትሰጥ ጉማና አማኝን ባሪያ ነፃ ማውጣት አለበት። ይህን ያላገኘ ሰው በተከታታይ ሁለት ወሮችን መፆም አለበት። አላህ ፀፀትን ለመቀበል ደነገገላችሁ። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው። አማኝን አስቦ የሚገድል ሰው ቅጣቱ በውስጧ ዘወታሪ ሲሆን ገሀነም ናት። አላህ በእርሱ ላይ ተቆጣ። ረገመውም። ለእርሱ ከባድ ቅጣትን* አዘጋጅቶለታል።

* የአላህ መልዕክተኛ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም ሰው ሕጋዊ ባልሆነ መንገድ የአንድን ሰው ነፍስ እስካላጠፋ ድረስ በሃይማኖቱ የነፃነት ጥላ ስር ነው»

ከሴቶች (92) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሐሪስ ቢን የዚድ የተባለ ግለሰብ ኢስላማዊ ዳዕዋን በመቃወም ነብዩን ያስቸግራቸው። በኋላ ከስህተቱ ለመመለስና ኢስላምን ለመቀበል ቁርጠኛ ሀሳብ ላይ ደረሰና ወደ መዲና ጉዞ ጀመረ። ሆኖም ወደ ነብዩ ሳይደርስ መንገድ ላይ ዓያሽ ቢን ረቢዕ የተባለ ሙስሊም ሃሳቡን ባለመረዳትና ቀደም ሲል በነበረው ቅሬታ ለተንኮል የመጣ መስሎት ገደለው። ከዚያም ስህተቱን አወቀና ችግሩን ለነብዩ ሲናገር ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ፤ ኢብኑል-ጀውዚ እና ሱዩጢ)

ከሴቶች ምዕራፍ (93) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሚቅየስ ኢብኑ ሱባባህ የተባለ ከወንድሙ ከሒሻም ጋር ኢስላምን ተቀብለው ሲኖሩ አንድ ዕለት ወንድሙን ባልታወቀ ምክንያት በበኒ ነጃሮች ሰፈር

*ተገድሎ አገኘው። በጉዳዩ በጣም አዝኖ ለነብዩ ሲነግራቸው ከበኒ ፊህሮች አንድ ሰው ጨምረው ወደ በኒ ነጃሮች «ገዳዩን ካወቃችሁ ስጡትና ደሙን ይመልስ ካልታወቀ ደግሞ የነፍስ ዋጋ ክፈሉት» በማለት ላኩባቸው። በኒ ነጃሮች ይህ ሲነገራቸው «እሺ ገዳዩን ስለማናውቀው የነፍስ ዋጋ እንከፍላለን» ብለው መቶ ግመል ከፈሉት። ሚቅየስ ግን ይህ አልበቃውም ነበርና በመንገድ ላይ እያሉ ሰይጣን ያሳስተዋል። «እንዴት የወንድምህን የነፍስ ዋጋ ተከፍለህ የሰው መሳለቂያ ትሆናለህ። ይልቅስ ይህን ሰው ግደልና የወንድምህን ደም መልስ። የወሰድከው የነፍስ ዋጋ ተጨማሪ ይሆንልሃል። በማለት ይሞግተዋል። እሱም ሰውዬውን በዲንጋይ ቀጥቅጦ ገድሎ ግመሎቹን ነድቶ እምነቱን ቀይሮ ወደ መካ በመግባቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ዋሒዲ፤ ኢብኑልጀውዚ እና ሱዩጢ። ይህ ሰው መካን ሙስሊሞች በተቆጣጠሩበት ቀን በካዕባ ተንጠልጥሎ ቢገኝም ግደሉት ያሉት ሰው ነው ይላሉ።*

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا ضَرَبۡتُمۡ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ فَتَبَيَّنُواْ وَلَا تَقُولُواْ لِمَنۡ أَلۡقَىٰٓ إِلَيۡكُمُ ٱلسَّلَٰمَ
لَسۡتَ مُؤۡمِنٗا تَبۡتَغُونَ عَرَضَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا فَعِندَ ٱللَّهِ مَغَانِمُ كَثِيرَةٞۚ كَذَٰلِكَ كُنتُم مِّن قَبۡلُ فَمَنَّ
ٱللَّهُ عَلَيۡكُمۡ فَتَبَيَّنُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٗا ﴿٩٤﴾ لَّا يَسۡتَوِي ٱلۡقَٰعِدُونَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ
غَيۡرُ أُوْلِي ٱلضَّرَرِ وَٱلۡمُجَٰهِدُونَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ بِأَمۡوَٰلِهِمۡ وَأَنفُسِهِمۡۚ فَضَّلَ ٱللَّهُ ٱلۡمُجَٰهِدِينَ
بِأَمۡوَٰلِهِمۡ وَأَنفُسِهِمۡ عَلَى ٱلۡقَٰعِدِينَ دَرَجَةٗۚ وَكُلّٗا وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلۡحُسۡنَىٰۚ وَفَضَّلَ ٱللَّهُ ٱلۡمُجَٰهِدِينَ عَلَى
ٱلۡقَٰعِدِينَ أَجۡرًا عَظِيمٗا ﴿٩٥﴾ دَرَجَٰتٖ مِّنۡهُ وَمَغۡفِرَةٗ وَرَحۡمَةٗۚ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورٗا رَّحِيمًا ﴿٩٦﴾

**94-96.** እናንተ በትክክል በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ በአላህ መንገድ ለመዋጋት በተጓዛችሁ ጊዜ አረጋግጡ። ሰላምታን ወደ እናንተ ላቀረበ ሰው የቅርቢቱን ሕይወት ጥቅም የምትፈልጉ ሆናችሁ ትክክለኛ አማኝ አይደለህም አትበሉት። አላህ ዘንድ ብዙ ዘረፋዎች አሉና። ከዚህ በፊት ልክ እንደዚሁ ነበራችሁ። አላህ በእናንተ ላይ ለገሰ። እናም ስለዚህ አረጋግጡ። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና። ከምዕመናን የጉዳት ባለቤት ከሆኑት በስተቀር ተቀማጮቹና በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉት ሰዎች አይስተካከሉም። በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የሚታገሉትን አላህ በተቀማጮቹ ላይ በደረጃ አበለጠ። ለሁሉም አላህ መልካሚቱን (ገነት) ተስፋ ሰጠ (ቃል ኪዳን ገባ)። ታጋዩቹንም በተቀማጮቹ ላይ አላህ በታላቅ ምንዳ አበለጠ። ከእርሱ ዘንድ በሆኑ ደረጃዎች አበለጠ። ምህረትንም አደረገ። እዝነትንም አዘነላቸው። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

*ከሴቶች ምዕራፍ (94) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ የሙስሊም ቡድኖች መንገድ ሲጓዙ አንድ ፍየል ጠባቂ መንገድ ላይ ያገኛሉ የፍየሉ ባለቤት «አሰላሙ አለይኩም» ሲላቸው ለጉዳዩ ትኩረት ባለ መስጠት ግለሰቡን ገድለው ፍየሎቹን ይዘው ሲሄዱ አላህ ተግባራቸውን ለማውገዝ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ቲርሚዚ እና ዋሒዲ)*

ከሴቶች ምዕራፍ (95) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዘይድ ቢን ሳቢት እንዳሉት ይህ አንቀፅ የወረደ ጊዜ «ከችግር ባለቤቶች ሌላ» የምትለው ቃል አብራ አልወረደችም ነበርና አብደላህ ኢብኑ መክቱም «እኔ አይነ ስውር ነኝ አላይም» በማለቱ ወዲያውኑ ነብዩን (ﷺ) ወህይ ሸፈናቸው። በእኔ ላይ ደገፍ ብለው ስለነበር የነበራቸው ክብደት ጭኔን እንዳይሰብረው እስከምሰጋ ድረስ ከብዶኝ ነበር። በዚያው «ከችግር ባለቤቶች ሌላ» የሚለው ቃል ወረደና አሁን ባለበት ቦታ ፃፉት ስለሉኝ ፃፍኩት ብሏል። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱلَّذِينَ تَوَفَّىٰهُمُ ٱلْمَلَـٰٓئِكَةُ ظَالِمِىٓ أَنفُسِهِمْ قَالُوا۟ فِيمَ كُنتُمْ ۖ قَالُوا۟ كُنَّا مُسْتَضْعَفِينَ فِى
ٱلْأَرْضِ ۚ قَالُوٓا۟ أَلَمْ تَكُنْ أَرْضُ ٱللَّهِ وَٰسِعَةً فَتُهَاجِرُوا۟ فِيهَا ۚ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ مَأْوَىٰهُمْ جَهَنَّمُ ۖ وَسَآءَتْ
مَصِيرًا ﴿٩٧﴾ إِلَّا ٱلْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ ٱلرِّجَالِ وَٱلنِّسَآءِ وَٱلْوِلْدَٰنِ لَا يَسْتَطِيعُونَ حِيلَةً
وَلَا يَهْتَدُونَ سَبِيلًا ﴿٩٨﴾ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَعْفُوَ عَنْهُمْ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَفُوًّا غَفُورًا ﴿٩٩﴾

**97-99.** እነዚያ ለእምነት ሲሉ ባለመሰደድ ነፍሶቻቸውን በዳዩች ሆነው መላዕክት የገደሏቸው መላዕክት ለእነርሱ በምን ነገር ላይ ነበራችሁ? ይሏቸዋል። በምድር ውስጥ ደካሞች ነበርን ይላሉ። የአላህ ምድር ትሰደዱባት ዘንድ ሰፊ አልነበረችምን? ይሏቸዋል። እነዚያም መኖሪያቸው ገሀነም ናት። ገሀነምም መመለሻነቷ ከፋች!። ከወንዶችና ከሴቶች ከህፃኖችም ሲሆኑ ከሀገራቸው ለመውጣት መላን የማይችሉና መንገድንም የማይመሩ ደካሞች ባለመሰደዳቸው ግን ምንም ቅጣት የለባቸውም። እነዚያ አላህ ከእነርሱ ይቅርታ ሊያደርግ ይሻል። አላህም ይቅር ባይና መሀሪ ነውና።

ከሴቶች ምዕራፍ (97) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰነ ቁጥር ያላቸው ግለሰቦች በነብዩ ዳዕዋ ተማርከው ኢስላምን ቢቀበሉም በመካ ውስጥ ለመኖር አስቸጋሪ ነበር። በዚህም የተነሳ እራሳቸውን ደብቀው ለመኖር ተገደዱ። ሆኖም የበድር ዘመቻ ዕለት በሙሽሪክ የመካ ጣዖታውያን ላይ በደረሰው አደጋ ሽንፈት የተናደዱ የመካ ጣዖታውያን እነዚህን ሙስሊሞች እየለቃቀሙና ከተደበቁበት እያወጡ አደጋ አደረሱባቸው። በዚህም ድርጊት ሙሰሊሞች እጅግ ሀዘን ተሰማቸው። ሆኖም አላህን ያመኑት ሰዎች ኢስላም በይፋ ለማራመድ ወደሚችሉበት መዲና ጨርቄን ማቄን ሳይሉ መውጣት ነበረባቸውና እነሱን በተመለከተ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ)

۞ وَمَن يُهَاجِرْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ يَجِدْ فِى ٱلْأَرْضِ مُرَٰغَمًا كَثِيرًا وَسَعَةً ۚ وَمَن يَخْرُجْ مِنۢ بَيْتِهِۦ
مُهَاجِرًا إِلَى ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ ثُمَّ يُدْرِكْهُ ٱلْمَوْتُ فَقَدْ وَقَعَ أَجْرُهُۥ عَلَى ٱللَّهِ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا
رَّحِيمًا ﴿١٠٠﴾ وَإِذَا ضَرَبْتُمْ فِى ٱلْأَرْضِ فَلَيْسَ عَلَيْكُمْ جُنَاحٌ أَن تَقْصُرُوا۟ مِنَ ٱلصَّلَوٰةِ إِنْ
خِفْتُمْ أَن يَفْتِنَكُمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ ۚ إِنَّ ٱلْكَـٰفِرِينَ كَانُوا۟ لَكُمْ عَدُوًّا مُّبِينًا ﴿١٠١﴾

**100-101.** በአላህ መንገድ የሚሰደድ ሰው ሁሉ በምድር ውስጥ ብዙ መሰደጃንና ምቾትን ያገኛል። ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው ስደተኛ ሆኖ ከቤቱ የሚወጣና ከዚያም በመንገድ ላይ ሞት የሚያገኘው ሰው ምንዳው በእርግጥ በአላህ ዘንድ ተረጋገጠ። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና። (አማኞች ሆይ!) በምድር ላይ በተጓዛችሁ ጊዜ እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሊያውኳችሁ እንደሚችሉ ብትፈሩ ከሰላቶች መካከል ከፊሎችን ባለ አራት ረካአ የሆኑትን ቁጥራቸውን ወደ ሁለት ሁለት በመቀነስ ብታሳጥሩ በእናንተ ላይ ኃጢአት የለም። ከሐዲያን ለእናንተ በእርግጥ ግልፅ ጠላቶች ናቸውና።

ከሴቶች ምዕራፍ (100) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ሐቢብ ብን ዱምረት አል ለይሲ የተባለ ሶሃባ በሽታ ነበረበት (በወቅቱም አሞት ነበር) ሙስሊሞችን ለጂሃድ (ለተቀደሰ ጦርነት) የሚያዘው አንቀፅ መውረዱን ሲሰማ ለልጆቹ «የዛሬን ሌሊት እንኳን በመካ አላድርም። ወደ መዲና ተሸክማችሁኝም ቢሆን ይዛችሁኝ ሂዱ» ይላቸዋል። እነርሱም ባላቸው መሰረት በቃሬዛ ተሸክመውት ሲሄዱ ተንኢም ከሚባል ስፍራ እንደደረሱ ሕይወቱ አለፈች። እናም ታሪኩ መዲና ለነበሩ ሙስሊሞች ሲደርሳቸው መዲና ደርሶ ቢሞት ኖሮ አጅሩ የተሟላ ይሆንለት ነበር በማለት ሀዘናቸውን በመግለፃቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። ዋሒዲ።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (92-100) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋናዋናዎች፦**

1. አንድ ሙዕሚን ልቡ እያወቀ የሌላውን ሙዕሚን ወንድሙን ነፍስ ማጥፋቱ ከፍተኛ ወንጀል ነው። በስህተት የሙዕሚንን ነፍስ ያጠፋ አንዲት ያመነችን ባሪያ ነፃ መውጣት ብቻ ይጠበቅበታል። ሆኖም ሟች ከሃዲ ቢሆንም ከሙስሊሙ ማህበረሰብ ጋር የቃል ኪዳን ስምምነት ከተፈራረመ ወገኖች አባል ከሆነ ገዳይ አንድ ባሪያ ነፃ ማውጣትና በተጨማሪም የነፍስ ዋጋ የመክፈል ግዴታ አለበት። ባሪያን ነፃ ማውጣት ያልቻለ ገዳይ ለሁለት ተከታታይ ወራት በመፆም ሊካካስለት ይችላል።
2. በስህተት ሳይሆን አውቆ በግፍ የሰውን ነፍስ ያጠፋ (ሰው የገደለ) ግን ለሟች ቤተሰቦች ካሳ የመክፈል ወይም የሞትን ቅጣት መቀበል ግዴታው መሆኑን፤
3. ለአላህ ዲን ሲባል የሚደረጉ ትግሎችና ስደቶች የሚያስገኙት ምንዳ ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ አላህ ዘንድ ተወዳጅ መሆናቸውን፤
4. በማንኛውም ጉዳይ የሚሰራጩ ወሬዎችን እንዳለ አምኖ መቀበል ተገቢ ያለመሆኑንና ተጨባጭ የሆነ ነገርን ለመያዝ ጉዳዩን ከስር መሰረቱ ማጣራት እንደሚገባ፤
5. አኼራዊ ጉዳዮችን በመተው ለምድራዊ ጥቅም ብቻ ቀን ተሌት መፍጋትና መሯሯጥ የተወገዘ መሆኑን፤
6. በሌሎች ሰዎች ከሚደርሱም አወንታዊም ሆነ አሉታዊ ክስተቶች መማር አስፈላጊ እንደሆነ፤
7. ሙጃሂዶች (ለአላህ ሀይማኖት የሚጋደሉ ወታደሮች) ከቀሪው ሙስሊም ህብረተሰብ የተለዩና ብልጫ ያላቸው እንደሆኑ፤
8. በበቂ ምክንያት ከጂሃድ ሜዳ ላይ ያልተገኙ ግን በሀሳባቸው በጦርነቱ ላይ ለመካፈል ቁርጠኛ ንያ ያላቸው ሰዎች በጦርነቱ ላይ ባይካፈሉም ልክ እንደ ተዋጊ ሙጃሂዶች ተመሳሳይ ምንዳ እንደሚያገኙ፤

9. የአምልኮት ተግባራት በነፃነት ለማከናወን እንዳይችሉ ሀይል ባለው ክፍል እገዳ የተደረገባቸው ሙስሊሞች ዒባዳቸውን በነፃነት ለማራመድ ወደ ሚችሉበት ሀገር መሰደድ ግዴታቸው መሆኑና ስደት የማድረግ ግዴታ ያለበት ከስደት መቅረቱ ወንጀል መሆኑን፤
10. ከጂሃድ ለመቅረት የሚያስችል በቂ ምክንያት ያላቸው ሙስሊሞች ከጂሃድ በመቅረታቸው እንደማይቀጡ ሁሉ ለመሰደድ በቂ ምክንያት የሌላቸው ሙስሊሞች ባለመሰደዳቸው ወንጀል እንደሌለባቸው፤
11. የአላህን ሃይማኖት ተግባራዊ ለማድረግ ሲባል መኖሪያ ሀገርን ለቆ ስደት መውጣት በአላህ ዘንድ ተወዳጅነትን እንደሚያስገኝና አጅሩም (ምንዳውም) ትልቅ መሆኑን፤
12. ሂጅራ ለመውጣት መንገድ ጀምሮ ሲያበቃ በመንገዱ ላይ የሞተ ሙስሊም ልክ ሙሉ ሂጅራ እንዳደረገ ሰው አይነት ምንዳ (ምንዳ) እንደሚሰጠው እንማራለን።

وَإِذَا كُنتَ فِيهِمْ فَأَقَمْتَ لَهُمُ ٱلصَّلَوٰةَ فَلْتَقُمْ طَآئِفَةٌ مِّنْهُم مَّعَكَ وَلْيَأْخُذُوٓا۟ أَسْلِحَتَهُمْ ۖ فَإِذَا
سَجَدُوا۟ فَلْيَكُونُوا۟ مِن وَرَآئِكُمْ وَلْتَأْتِ طَآئِفَةٌ أُخْرَىٰ لَمْ يُصَلُّوا۟ فَلْيُصَلُّوا۟ مَعَكَ وَلْيَأْخُذُوا۟
حِذْرَهُمْ وَأَسْلِحَتَهُمْ ۗ وَدَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَوْ تَغْفُلُونَ عَنْ أَسْلِحَتِكُمْ وَأَمْتِعَتِكُمْ فَيَمِيلُونَ
عَلَيْكُم مَّيْلَةً وَٰحِدَةً ۚ وَلَا جُنَاحَ عَلَيْكُمْ إِن كَانَ بِكُمْ أَذًى مِّن مَّطَرٍ أَوْ كُنتُم مَّرْضَىٰٓ
أَن تَضَعُوٓا۟ أَسْلِحَتَكُمْ ۖ وَخُذُوا۟ حِذْرَكُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ أَعَدَّ لِلْكَٰفِرِينَ عَذَابًا مُّهِينًا ﴿١٠٢﴾

**102.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ) በጦርነት ላይ በውስጣቸው በሆንክና ሶላትን ለእነርሱ ባሰገድካቸው ጊዜ ከእነርሱ አንዲት ቡድን ከአንተ ጋር ይቁም። መሳሪያዎቻቸውንም ይያዙ። ሱጁድ ባደረጉ ጊዜ ከበስተኋላችሁ ይሁኑ። ከዚያም እነዚያ ቡድኖች ይሂዱና ያልሰገዱት ሌሎች ቡድኖች ይምጡ ከዚያም ከአንተ ጋር ይስገዱ። ጥንቃቄያቸውንና መሳሪያዎቻቸውንም ይያዙ። እነዚያ በአላህ የካዱት ከትጥቅና ስንቃችሁ ብትዘናጉና በአንድ ጊዜ ቢወሯችሁ ይመኛሉ። ዝናብ አውኳችሁ ወይም በሽተኛ ሆናችሁ ትጥቃችሁን ብታስቀምጡ በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም። ጥንቃቄ አድርጉ። አላህ ለካሐዲያን አዋራጅን ቅጣት አዘጋጀ።

ከሴቶች ምዕራፍ ከ **(101-102)** ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- ሙስሊሞች በተለያዮ አጋጣሚዎች ወደ ተለያዩ ሀገራት ጉዞ ስለሚያደርጉ «እንዴት እንስገድ» ብለው መልዕክተኛውን ሲጠይቋቸው ነው እነህ አናቅፅ የውረዱት። ከዚም አንድ ዓመት ከቆዩ በኋላ ነብዩ (ﷺ) ዘመቻ ወጥተው እያሉ ሶላት ደርሶ ሲሰግዱ ከሙሽሪኮች «ይህን ጊዜ ነው በድንገት መምታት ወይም መጨረስ» በማለት ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ «ግዴለም አንፀትም ተመሳሳይ ሶላቶች ስላሉ በሚቀጥለው ሶላት ላይ እንጨፈጭፋቸዋለን» ብለው ተስማምተው ባሉበት አላህ ለካፊሮች ጥቃት እንዳይጋለጡ አመቻችቶ የሶላትን ስርዓት በምን መልኩ መስገድ እንዳለባቸው እነዚህን አናቅፅ አወረደ፡ (አቡዳውድ፤ ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ።)

فَإِذَا قَضَيْتُمُ ٱلصَّلَوٰةَ فَٱذْكُرُواْ ٱللَّهَ قِيَـٰمًا وَقُعُودًا وَعَلَىٰ جُنُوبِكُمْ ۚ
فَإِذَا ٱطْمَأْنَنتُمْ فَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ ۚ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ كَانَتْ عَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ كِتَـٰبًا مَّوْقُوتًا ﴿١٠٣﴾

**103.** እናም ሶላትን በፈፀማችሁ ጊዜ ቆማችሁ፣ ተቀምጣችሁና በጎኖቻችሁ ተጋድማችሁ አላህን አውሱ። በተረጋጋችሁም ጊዜ ሶላትን ደንቧን አሟልታችሁ ስገዱ። ሶላት በምዕመናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናትና።

وَلَا تَهِنُواْ فِى ٱبْتِغَآءِ ٱلْقَوْمِ ۖ إِن تَكُونُواْ تَأْلَمُونَ فَإِنَّهُمْ يَأْلَمُونَ كَمَا تَأْلَمُونَ ۖ
وَتَرْجُونَ مِنَ ٱللَّهِ مَا لَا يَرْجُونَ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا ﴿١٠٤﴾

**104.** ሰዎችን ከመፈለግ አትስነፉ። ስትቆስሉ የምትታመሙ ብትሆኑም እናንተ እንደምትታመሙ ሁሉ እነርሱም ይታመማሉ። እናንተ ግን እነርሱ የማይከጅሉትን ከአላህ ትከጅላላችሁ። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው።

إِنَّآ أَنزَلْنَآ إِلَيْكَ ٱلْكِتَـٰبَ بِٱلْحَقِّ لِتَحْكُمَ بَيْنَ ٱلنَّاسِ بِمَآ أَرَىٰكَ ٱللَّهُ ۚ وَلَا تَكُن لِّلْخَآئِنِينَ
خَصِيمًا ﴿١٠٥﴾ وَٱسْتَغْفِرِ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿١٠٦﴾ وَلَا تُجَـٰدِلْ عَنِ ٱلَّذِينَ يَخْتَانُونَ
أَنفُسَهُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ مَن كَانَ خَوَّانًا أَثِيمًا ﴿١٠٧﴾ يَسْتَخْفُونَ مِنَ ٱلنَّاسِ وَلَا يَسْتَخْفُونَ مِنَ
ٱللَّهِ وَهُوَ مَعَهُمْ إِذْ يُبَيِّتُونَ مَا لَا يَرْضَىٰ مِنَ ٱلْقَوْلِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِمَا يَعْمَلُونَ مُحِيطًا ﴿١٠٨﴾ هَـٰٓأَنتُمْ
هَـٰٓؤُلَآءِ جَـٰدَلْتُمْ عَنْهُمْ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا فَمَن يُجَـٰدِلُ ٱللَّهَ عَنْهُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ أَم مَّن يَكُونُ
عَلَيْهِمْ وَكِيلًا ﴿١٠٩﴾ وَمَن يَعْمَلْ سُوٓءًا أَوْ يَظْلِمْ نَفْسَهُۥ ثُمَّ يَسْتَغْفِرِ ٱللَّهَ يَجِدِ ٱللَّهَ غَفُورًا
رَّحِيمًا ﴿١١٠﴾ وَمَن يَكْسِبْ إِثْمًا فَإِنَّمَا يَكْسِبُهُۥ عَلَىٰ نَفْسِهِۦ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا ﴿١١١﴾
وَمَن يَكْسِبْ خَطِيٓـَٔةً أَوْ إِثْمًا ثُمَّ يَرْمِ بِهِۦ بَرِيٓـًٔا فَقَدِ ٱحْتَمَلَ بُهْتَـٰنًا وَإِثْمًا مُّبِينًا ﴿١١٢﴾

**105-112.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ፦) እኛ በሰዎች መካከል አላህ ባሳወቀህ ልትፈርድ ወደ አንተ መጽሐፍን በእውነት አወረድን። እናም ለከዳተኞች ተከራካሪ አትሁን። አላህን ምህረት ለምን።* አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና። ለእነዚያ ነፍሶቻቸውን ለሚበድሉት ሰዎች አትከራከር። አላህ ከዳተኛንና ኃጢአተኛን ሰው አይወድምና። ከሰው ይደበቃሉ። አላህ በዕውቀቱ ከእነርሱ ጋር ሲሆን ከንግግር የማይወደውን ነገር (በልቦቻቸው) በሚያሳድሩ ጊዜ ከእርሱ አይደበቁም። አላህ በሚሰሩት ሁሉ በእውቀቱ ከባቢ ነውና።

እነሆ እናንተ እነዚያ በቅርቢቱ ሕይወት ውስጥ ስለ እነርሱ ተከራከራችሁ። በትንሳኤ ቀን አላህን ስለ እነርሱ የሚከራከርላቸው ማን ነው? ወይስ ለእነርሱ ሀላፊ የሚሆን ማን ነው? መጥፎ ነገር የሚሰራ ሰው ሁሉ ወይም ነፍሱን የሚበድልና ከዚያም ተፀፅቶ አላህን ምህረት የሚለምን ሰው አላህን መሀሪና አዛኝ ሆኖ ያገኘዋል። ኃጢአትንም የሚሰራ ሰው ሁሉ የሚሰራው ጥፋት ጉዳቱ በራሱ ላይ ብቻ ነው። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና። ኃጢአትን ወይም ወንጀልን የሚሰራና ከዚያም በእርሱ ንፁህን ሰው የሚሰድብ ሰው ቅጥፈትንና ግልፅ ኃጢአትን በቁርጥ ተሸከመ።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «በአንድ ቀን ውስጥ የአላህን ምህረትና ወደ አላህ መመለስን ከሰባ ጊዜ በላይ እጠይቃለሁ።»

وَلَوْلَا فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكَ وَرَحْمَتُهُۥ لَهَمَّت طَّآئِفَةٌ مِّنْهُمْ أَن يُضِلُّوكَ وَمَا يُضِلُّونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمْ ۖ وَمَا يَضُرُّونَكَ مِن شَيْءٍ ۚ وَأَنزَلَ ٱللَّهُ عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَعَلَّمَكَ مَا لَمْ تَكُن تَعْلَمُ ۚ وَكَانَ فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكَ عَظِيمًا ﴿١١٣﴾ ۞ لَّا خَيْرَ فِى كَثِيرٍ مِّن نَّجْوَىٰهُمْ إِلَّا مَنْ أَمَرَ بِصَدَقَةٍ أَوْ مَعْرُوفٍ أَوْ إِصْلَٰحٍۭ بَيْنَ ٱلنَّاسِ ۚ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ ٱبْتِغَآءَ مَرْضَاتِ ٱللَّهِ فَسَوْفَ نُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا ﴿١١٤﴾

**113-114.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የአላህ ችሮታና እዝነቱ በአንተ ላይ ባልነበረ ኖሮ ከእነርሱ የሆኑ ቡድኖች ሊያሳስቱህ ባሰቡ ነበር። ነፍሶቻቸውን እንጂ ሌላ አያሳስቱም። በምንም አይጎዱህም። አላህ በአንተ ላይ መጽሐፍንና ጥበብን አወረደ። የማታውቀውን ሁሉ አስተማረህ። የአላህ ችሮታ በአንተ ላይ ታላቅ ነው። ከውይይቶቻቸው መካከል በምፅዋት ወይም በበጎ ስራ ወይም በሰዎች መካከል በማስታረቅ ከሚያዙ ሰዎች ውይይት በስተቀር በብዙው ውይይት ውስጥ ደግ ነገር የለበትም። ይህንንም የተባለውን የአላህን ውዴታ ለመፈለግ የሚሰራ ሰው ታላቅ ምንዳን እንሰጠዋለን።

وَمَن يُشَاقِقِ ٱلرَّسُولَ مِنۢ بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُ ٱلْهُدَىٰ وَيَتَّبِعْ غَيْرَ سَبِيلِ ٱلْمُؤْمِنِينَ نُوَلِّهِۦ مَا تَوَلَّىٰ وَنُصْلِهِۦ جَهَنَّمَ ۖ وَسَآءَتْ مَصِيرًا ﴿١١٥﴾

**115.** ቅኑ መንገድ ለእነርሱ ከተገለፀ በኋላ መልዕክተኛውን የሚጨቃጨቅና ከምዕመናኖቹ መንገድ ሌላ የሆነን የሚከተል ሰው ሁሉ በዚህ ዓለም በመረጠው ጥመት ላይ እንተወዋለን። በሁለተኛው ዓለምም ወደ ገሀነም እናስገባዋለን። መመለሻይቱም ገሀነም ከፋች!፣

إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَغۡفِرُ أَن يُشۡرَكَ بِهِۦ وَيَغۡفِرُ مَا دُونَ ذَٰلِكَ لِمَن يَشَآءُۚ
وَمَن يُشۡرِكۡ بِٱللَّهِ فَقَدۡ ضَلَّ ضَلَٰلَۢا بَعِيدًا ﴿١١٦﴾

**116.** አላህ በእርሱ ማጋራትን ፈፅሞ አይምርም። ከሽርክ በታች ሌላ ያለውን ጥፋት ግን ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህ የሚያጋራ ሰው ከእውነት የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።

ከሴቶች ምዕራፍ ከ (105-116) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ጡዕመት ቢን ኡብይሪቅ የተባለ ሰው ቀእዳህ ከተባለው ሶሃባ ቤት ልብስና ዱቄት ከሰረቀ በኋላ እንዳይታወቅበት አንድ አይሁዳዊ ቤት ውስጥ ይደብቀዋል። ሆኖም በተደረገው ክትትል ንብረቱ ከደበቀበት ቦታ ተገኘ። ንብረቱ የተገኘበት አይሁድም ጡዕመት ቢን ኡብይሪቅ እንዳስቀመጠው አስመስክሮ ተናገረ። የጡዕመት ዘመዶች ግን ጡዕመት ሌባ እንዳልሆነ ከደሙ ንፁህ መሆኑን ከተናገሩ በኋላ ነብዩ ለጡዕመት ጥበቃ እንዲያደርጉለት አማላጅ ሆነው ቀረቡ። በዚህ ወቅት ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። ከዚያም ይህ ግለሰብ ወደ መካ ሸሽቶ ፈረጠጠ። እምነቱንም ቀየረ በመካ ቆይታውም የለመደውን ሌብነት አጧጡፎ ቀጠለና በመጨረሻም እንደለመደው በሌሊት ለመስረቅ የሰው ቤት ሲሰብር ግድግዳው ወድቆበት ሞተ። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር፤ ኢብኑልጀውዚ እና ሱዩጢ)

إِن يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦٓ إِلَّآ إِنَٰثٗا وَإِن يَدۡعُونَ إِلَّا شَيۡطَٰنٗا مَّرِيدٗا ﴿١١٧﴾ لَّعَنَهُ ٱللَّهُۘ وَقَالَ
لَأَتَّخِذَنَّ مِنۡ عِبَادِكَ نَصِيبٗا مَّفۡرُوضٗا ﴿١١٨﴾ وَلَأُضِلَّنَّهُمۡ وَلَأُمَنِّيَنَّهُمۡ وَلَأٓمُرَنَّهُمۡ فَلَيُبَتِّكُنَّ
ءَاذَانَ ٱلۡأَنۡعَٰمِ وَلَأٓمُرَنَّهُمۡ فَلَيُغَيِّرُنَّ خَلۡقَ ٱللَّهِۚ وَمَن يَتَّخِذِ ٱلشَّيۡطَٰنَ وَلِيّٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِ
فَقَدۡ خَسِرَ خُسۡرَانٗا مُّبِينٗا ﴿١١٩﴾ يَعِدُهُمۡ وَيُمَنِّيهِمۡۖ وَمَا يَعِدُهُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ إِلَّا غُرُورًا ﴿١٢٠﴾
أُوْلَٰٓئِكَ مَأۡوَىٰهُمۡ جَهَنَّمُ وَلَا يَجِدُونَ عَنۡهَا مَحِيصٗا ﴿١٢١﴾

**117-121.** ከእርሱ ሌላ እንስት ጣኦታትን እንጂ አይገዙም። አመጸኛ ሰይጣንንም እንጂ ሌላን አይገዙም። አላህ የረገመውን ከባሮችህም የተወሰነን ድርሻ በእርግጥ እይዛለሁ ያለውን (ሰይጣን እንጂ ሌላን አይከተሉም)። በእርግጥ አጠማቸዋለሁ። ከንቱን ምኞትም አስመኛቸዋለሁ። አዛቸውምና የእንስሶችን ጆርባዎች ይተለትላሉ። አዛቸውምና የአላህን ፍጥረት ይለውጣሉ። (ያለውን ይከተላሉ) ከአላህም ሌላ ሰይጣንን ረዳት አድርጎ የሚይዝ ሰው ግልፅ ኪሳራ በእርግጥ ከሰረ። የማይፈፅመውን ከንቱ ተስፋ ይሰጣቸዋል። ያስመኛቸዋልም። ሰይጣን ለማታለል እንጂ ቃል አይገባላቸውም። እነዚያ የመጨረሻ መኖሪያቸው ገሀነም ናት። ከእርሷም መሸሻን አያገኙም።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (101-121) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋናዋናዎች፡-**

1. ከተለመደው የሶላት አሰጋገድ በተለየ መልኩ ለመንገደኞች እና በጦርነት ውስጥ ለሚገኙ ወታደሮች እንዲሰግዱ የተፈቀደላቸው አጠር ያለ ሶላት (ረከአው ይቀንሳል) አፈፃፀሙና ስርአቱ ምን እንደሚመስል፤
2. የጀመዓ ሶላት እጅግ ተፈላጊ የሆነ የኢስላም ድንጋጌ መሆኑንና የተሰጠውን ታላቅ ቦታ፤
3. በማንኛውም ወቅት አላህን ማስታወስ ተገቢ ቢሆንም ከሶላት በኋላ ግን የበለጠና ተመራጭ እንደሆነ፤
4. ሶላት ከዋና ዋና የኢስላም መሰረታዊ ተግባራ አንዱ በመሆኑ ወቅቱን ጠብቆ መስገድ እንዲሁ ግዴታ መሆኑን፤
5. በጠላት ፊት ድክመትን ማንፀባረቅና የሽንፈት ፊት ማሳየት የተከለከለ መሆኑን፤
6. ምንም ያህል ስጋዊ ወይም ግለሰባዊ ቀረቤታ ቢኖረውም ከሃዲ ለሆነ ሰው በመሆኑ ጥላቻን እንጂ ውዴታን ማሳየት ተገቢ ያለመሆኑን፤ ለከሓዲያን ድጋፍ ለመስጠትና ለመርዳት እንዲሁም ከጎናቸው ለመቆም ማሰብ የማይፈቀድ መሆኑን፤
7. ንስሀ መግባት ከንስሀ በፊት የተሰሩ ኃጢአቶችን በሙሉ እንደሚያሰርዝና ይቅርታን ከአላህ እንደሚያስገኝ ኢስላም ያስገነዝባል። አሉባልታ በህብረተሰቡ ዘንድ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳትና ተፅዕኖ ከባድ መሆኑን፤ እንዲሁም ግፍ መስራትና በደል በመጨረሻ ለባለቤቱ ጉዳትን የሚያተርፍለት መሆኑን፤
8. ለሁለት ሰዎች ብቻ የሚቀር ሚስጥራዊ ሴራና ወሬ መሸረብ የተከለከለ መሆኑንና ለመልካም ስራዎችና ተያያዥ ለሆኑ ኢስላማዊ ተግባራት ካልሆነ በስተቀር በሌሎች ርዕሶች ላይ የሚደረጉ ሚስጥራዊ ስብሰባዎች ሁሉ ፋይዳ ቢስ መሆናቸውን፤
9. እውነታን ከተረዳ በኋላ በትዕቢት በመነሳሳት ነብዩን (ﷺ) የሚከራከር ሁሉ ከሀቅ ያፈነገጠ መሆኑን፤
10. ሺርክ የሌለበት ሰው ወንጀል ቢሰራና ቢሞት እንኳን የአላህ ፈቃድ ከሆነ ወንጀሎቹን በሙሉ ሊምረው ይችላል። ጣኦትንና ስሜታቸውን የሚያመልኩ ባዕድ አምላኪዎች የሰይጣን ተገዥ መሆናቸውን፤
11. ንቅሳትን መነቀስና ማኮላሸትን በሰውነታችን ላይ መፈፀም የተከለከለ መሆኑን፤
12. በጫማ ላይ ማበስ ከኢስላማዊ ህግጋቶች አንዱ ነው። የውዱእ አንቀፅ በሚባለው አንቀፅ ላይ እግሮችን ከሚለው ቦታ «እጠቡ»ከማለት ፋንታ «አበሱ» የሚልን መልዕክት የሚያስተላልፍ አግባብ እንዳለው በትክክለኛ ሰነድ ተዘግቧል። ከዚህም በመነሳት እግርን ማበስ እንጂ ማጠብ ግዴታ አይደለም ወደ ማለት የሄዱ ክፍሎች አሉ። ሆኖም ግን ንባቡ ትክክል ቢሆንም ትርጉሙ ግን በእግራችሁ ላይ «አበሱ» ማለት ሳይሆን በጫማዎችና እነሱን በሚመስሉ ነገሮች ላይ ማበስን እንደሆነ የማይክዱ ሲሆን ብዙ ጊዜ ስለ እዚህ ድርጊት ያላቸው ግንዛቤ የተሳሳተ እየሆነ ከትክክለኛው መስመር እየለቀቀ ይሄዳል። ይህም ስህተት እየተስፋፋና እየሰፋ ሂዶ ከአላህ ጋር ሌላን ነገር ወደ ማጋራት ይደርሳሉ። ለዚህ ነው አላህ ይህን መሰል ስህተት ለማስተካከል ነብያትን በየጊዜው የላከው።

وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ سَنُدْخِلُهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ
فِيهَآ أَبَدًا ۖ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقًّا ۚ وَمَنْ أَصْدَقُ مِنَ ٱللَّهِ قِيلًا ﴿١٢٢﴾

122. እነዚያ በአላህ ያመኑትና በጎ ስራዎችን የሰሩ ሁሉ በስራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች ዘላለም በውስጣቸው ዘወታሪዎች ሲሆኑ እናስገባቸዋለን። አላህ እውነተኛን ተስፋ ሰጣቸው። በንግግርም ከአላህ ይበልጥ እውነተኛ ማን ነው?።

لَّيْسَ بِأَمَانِيِّكُمْ وَلَآ أَمَانِيِّ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ ۗ مَن يَعْمَلْ سُوٓءًا يُجْزَ بِهِۦ وَلَا يَجِدْ لَهُۥ مِن
دُونِ ٱللَّهِ وَلِيًّا وَلَا نَصِيرًا ﴿١٢٣﴾ وَمَن يَعْمَلْ مِنَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ مِن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ
فَأُو۟لَٰٓئِكَ يَدْخُلُونَ ٱلْجَنَّةَ وَلَا يُظْلَمُونَ نَقِيرًا ﴿١٢٤﴾

123-124. (ነገሩ) በምኞታችሁና በመጽሐፍ ሰዎች ምኞት አይደለም። መጥፎን የሚሰራ ሰው ሁሉ በእርሱ ይቀጣል። ለእርሱም ከአላህ ሌላ ጠባቂንም ረዳትንም አያገኝም። ወይም ከሴት አማኝ ሆነው ከበጎ ስራዎች አንድን ነገር የሚሰሩ ሰዎች ገነት ይገባሉ። በተምር ፍሬ ላይ ያለችን ነጥብ* ያክል እንኳን አይበደሉም።

* በዚሁ ሱራ (53) ኛው አንቀፅ ላይ በሰፊው አልፏል።

ከሴቶች (123) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ትክክለኛ አማኞች የመጽሐፍት ባለቤቶች ሁለቱም በየበኩላቸው እየተነሱ «የእኛ ጉዳይ ብቻ ነው ትክክል» በማለት ፉክክር ሲያደርጉ አላህ ፍርዱን ለመስጠት ይህን አንቀፅ አወረደ። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከሴቶች ምዕራፍ (124) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በሱረቱ ኒሳዕ (123) ኛው ላይ ያለው አንቀፅ ሲወርድ መጽሐፍ ባለቤቶች እኛ እና እናንተ እኩል ነን እኮ ስላሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَمَنْ أَحْسَنُ دِينًا مِّمَّنْ أَسْلَمَ وَجْهَهُۥ لِلَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ وَٱتَّبَعَ مِلَّةَ إِبْرَٰهِيمَ حَنِيفًا ۗ وَٱتَّخَذَ ٱللَّهُ
إِبْرَٰهِيمَ خَلِيلًا ﴿١٢٥﴾ وَلِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ مُّحِيطًا ﴿١٢٦﴾

125-126. እርሱ መልካም ሰሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ ከሰጠና የኢብራሂምንም መንገድ ቀጥተኛ ሲሆን ከተከተለ ሰው ይበልጥ ሃይማኖቱ ያማረ ማን ነው? አላህ ኢብራሂምን ፍፁም ወዳጅ አድርጎ ያዘው። በሰማያትና በምድር ያለው ነገር ሁሉ የአላህ ነው። አላህ በነገሩ ሁሉ በእውቀት ከባቢ ነው።

وَيَسْتَفْتُونَكَ فِى ٱلنِّسَآءِ ۖ قُلِ ٱللَّهُ يُفْتِيكُمْ فِيهِنَّ وَمَا يُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ فِى ٱلْكِتَٰبِ فِى يَتَٰمَى
ٱلنِّسَآءِ ٱلَّٰتِى لَا تُؤْتُونَهُنَّ مَا كُتِبَ لَهُنَّ وَتَرْغَبُونَ أَن تَنكِحُوهُنَّ وَٱلْمُسْتَضْعَفِينَ مِنَ
ٱلْوِلْدَٰنِ وَأَن تَقُومُوا۟ لِلْيَتَٰمَىٰ بِٱلْقِسْطِ ۚ وَمَا تَفْعَلُوا۟ مِنْ خَيْرٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِهِۦ عَلِيمًا ﴿١٢٧﴾

**127.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ) ስለ ሴቶች ጉዳይ ይጠይቁሃል። አላህ ስለነሱ ይነግራችኋል። ያም በመጽሐፍ ውስጥ በእናንተ ላይ የሚነበበው ሲሆን በእነዚያ ከውርስ የተደነገገላቸውን ድርሻ በማትሰጧቸው ሴቶችና ልታገቧቸው በማትፈልጉት የቲሞች ሴቶች ይህንን እንዳታደርጉና ህፃናት ለሆኑትም ደካሞች መብታቸውን እንድትሰጡ ለየቲሞች በትክክል እንድትቆሙ ይነገራችኋል በላቸው። ከበጎም ስራ የሆነን ማንኛውንም ስራ ብትሰሩ አላህ እርሱን አዋቂ ነው።

*ከሴቶች ምዕራፍ (127) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ ሶሃባዎች ነብዩን (ﷺ) መጥተው «የሴቶቹ ውርስና ሌሎችን ጉዳያቸውን በተመለከተ» እንዲያስተምሯቸው ስለጠየቋቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።*

وَإِنِ ٱمۡرَأَةٌ خَافَتۡ مِنۢ بَعۡلِهَا نُشُوزًا أَوۡ إِعۡرَاضًا فَلَا جُنَاحَ عَلَيۡهِمَآ أَن يُصۡلِحَا بَيۡنَهُمَا
صُلۡحًاۚ وَٱلصُّلۡحُ خَيۡرٌۗ وَأُحۡضِرَتِ ٱلۡأَنفُسُ ٱلشُّحَّۚ وَإِن تُحۡسِنُواْ وَتَتَّقُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِمَا
تَعۡمَلُونَ خَبِيرًا ١٢٨ وَلَن تَسۡتَطِيعُوٓاْ أَن تَعۡدِلُواْ بَيۡنَ ٱلنِّسَآءِ وَلَوۡ حَرَصۡتُمۡۖ فَلَا تَمِيلُواْ كُلَّ
ٱلۡمَيۡلِ فَتَذَرُوهَا كَٱلۡمُعَلَّقَةِۚ وَإِن تُصۡلِحُواْ وَتَتَّقُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ غَفُورًا رَّحِيمًا ١٢٩ وَإِن
يَتَفَرَّقَا يُغۡنِ ٱللَّهُ كُلًّا مِّن سَعَتِهِۦۚ وَكَانَ ٱللَّهُ وَٰسِعًا حَكِيمًا ١٣٠

**128-130.** ሴት ልጅ ከባሏ ጥላቻን ወይም ከእርሷ ፊቱን ማዞሩን ብታውቅ እና ከዚያ በመካከላቸው እንደገና ቢስማሙ በሁለቱ ላይ ኃጢአት የለባቸውም። መታረቅ መልካም ነውና። ነፍሶች ሁሉ ንፍገት ተጣለባቸው። (ባሎች ሆይ!፣) መልካም ነገር ብትሰሩና ብትጠነቀቁ ግን አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው። (ባሎች ሆይ፣) በሁለትና ከዚያ በላይ በሆኑ ሴቶች መካከል ምንም እንኳን ብትጓጉ (በፍቅር) ለማስተካከል አትችሉም። ሆኖም የጠላችኋትን ሴት እንደተንጠለጠለች ገመድ አድርጋችሁ ትተዋት ዘንድ ወደምትወዷት ሴት ብቻ ሙሉ መዘንበልን አትንዘንበሉ። ብታበጁና ብትጠነቀቁ አላህ መሀሪና አዛኝ ነው። ባልና ሚስት በመሀከላቸው በተፈጠረው ችግር ቢለያዩ አላህ ሁሉንም በችሮታው ያብቃቃቸዋል። አላህ ችሮታው ሰፊና ጥበበኛ ነውና።

*ከሴቶች ምዕራፍ (128) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ ባለ ትዳሮች አብሮ ለመኖርም ሆነ ለመለያየት ከሚያስቸግር ሁኔታ ላይ ሲደርሱ ሴቷ «አትፍታኝ አንተ ግን ለእኔ የምትችለውን አድርግልኝ» በማለት መፍትሄ በምታመጣ ሴት ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)*

وَلِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۗ وَلَقَدْ وَصَّيْنَا ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلِكُمْ وَإِيَّاكُمْ
أَنِ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۚ وَإِن تَكْفُرُوا۟ فَإِنَّ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ غَنِيًّا حَمِيدًا ﴿١٣١﴾

**131.** በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው። እነዚያንም ከበፊታችሁ መጽሐፍ የተሰጡትን እናንተንም አላህን ፍሩ በማለት በእርግጥ አዘዝን። ብትክዱም በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው (አትጎዱትም)። አላህም በራሱ ተብቃቂና ምስጉን ነውና።

وَلِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَكِيلًا ﴿١٣٢﴾ إِن يَشَأْ يُذْهِبْكُمْ أَيُّهَا ٱلنَّاسُ
وَيَأْتِ بِـَٔاخَرِينَ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ ذَٰلِكَ قَدِيرًا ﴿١٣٣﴾ مَّن كَانَ يُرِيدُ ثَوَابَ ٱلدُّنْيَا فَعِندَ ٱللَّهِ ثَوَابُ
ٱلدُّنْيَا وَٱلْـَٔاخِرَةِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ سَمِيعًۢا بَصِيرًا ﴿١٣٤﴾

**132-134.** በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። መመኪያነትም በአላህ በቃ። እናንተ ሰዎች ሆይ፣ አላህ ቢሻ ያስወግዳችሁና ሌሎችንም በቦታችሁ ላይ ይተካል። አላህ በዚህ ላይ ቻይ ነው። የቅርቢቱን አለም ምንዳ የሚፈልግ ሰው ሁሉ አላህ ዘንድ የቅርቢቱና የመጨረሻይቱ ምንዳ አለ። አላህ ሰሚ እና ተመልካች ነውና።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (122-134) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎች፡-**

1. በልብ ውስጥ ሰርፆ የገባ ትክክለኛው እምነት ወደ ጀነት የሚያስገባው በር መሆኑን፤ ቃልን ማክበርና በሰጡት ቃል መሰረት መገኘት ግዴታ መሆኑንና ንግግራችን በሙሉ በእውነት ላይ የተመሰረተ መሆን እንዳለበት፤
2. የአላህ ፀጋ ተድላ የሚገኘው በባዶ ተስፋና ምኞት ሳይሆን በትክክለኛ እምነትና በመልካም ስራ መሆኑን፤
3. ኢስላምን ከሌሎች እምነቶች በሙሉ ብልጫ ያለው ንፁህና ቀጥተኛ ሃይማኖት መሆኑን፤
4. ነብዩ ኢብራሂም አላህ ዘንድ ከፍ ያለ ማዕረግና ክብር ያላቸው ነብይ እንደሆኑ፤
5. አላህ ከማንኛውም አካል ድጋፍን የማይፈልግ የተብቃቃ ኃያልና ሀብታም ጌታ መሆኑን፤
6. ሴቶችና ሕፃናት የንብረትና የገንዘብ ውርስ የተፈቀደላቸው መሆኑን፤
7. በባልና በሚስት መሀከል የሚፈጠሩ ግጭቶችና አለመግባባቶች በእርቅ መፍታት ተገቢ መሆኑን፤
8. ሁለት ሚስቶች ያሉት ቁሳዊ ነገሮችን በተገቢው መልኩና በፍትሀዊነት ማድረሱ ግዴታው ቢሆንም በፍቅርና በግብረ ስጋ ግንኙነት በተመለከተ ግን የማይጠየቅበት መሆኑን፤
9. አላህን በመፍራት የወንጀል ድርጊቶችን ሲፈፅሙ መመልከት ሳይሆን መከልከል ግዴታ መሆኑን፤
10. አላህ በምድር ላይ ያሉ ህዝቦችን በሙሉ አስወግዶ ሌላ አዲስ ሕዝብ ለመፍጠር የሚችል ኃያል ጌታ መሆኑን፤
11. ስራዎች በሙሉ በፍፁምነት ለአላህ ብቻ ተብለው መሰራት እንዳለባቸው እንማራለን።

۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُواْ قَوَّٰمِينَ بِٱلْقِسْطِ شُهَدَآءَ لِلَّهِ وَلَوْ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُمْ أَوِ ٱلْوَٰلِدَيْنِ وَٱلْأَقْرَبِينَ ۚ إِن يَكُنْ غَنِيًّا أَوْ فَقِيرًا فَٱللَّهُ أَوْلَىٰ بِهِمَا ۖ فَلَا تَتَّبِعُواْ ٱلْهَوَىٰٓ أَن تَعْدِلُواْ ۚ وَإِن تَلْوُۥٓاْ أَوْ تُعْرِضُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرًا ﴿١٣٥﴾

**135.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በትክክል (ለፍትህ) ቋሚዎች በነፍሶቻችሁ ወይም በወላጆችና በቅርብ ዘመዶች ላይ ቢሆንም እንኳ ለአላህ መስካሪዎች ሁኑ። ሀብታም ወይም ድሃ ቢሆን አላህ በእነርሱ ለእናንተ ይበልጥ ተገቢ ነው። እንዳታዳሉም ዝንባሌን አትከተሉ። ምስክርን ብታጣምሙ ወይም (መመስከርን) ብትተው አላህ በምትሰሩት ነገር ላይ ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ ءَامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلْكِتَٰبِ ٱلَّذِى نَزَّلَ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ وَٱلْكِتَٰبِ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ مِن قَبْلُ ۚ وَمَن يَكْفُرْ بِٱللَّهِ وَمَلَٰٓئِكَتِهِۦ وَكُتُبِهِۦ وَرُسُلِهِۦ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ فَقَدْ ضَلَّ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا ﴿١٣٦﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ثُمَّ كَفَرُواْ ثُمَّ ءَامَنُواْ ثُمَّ كَفَرُواْ ثُمَّ ٱزْدَادُواْ كُفْرًا لَّمْ يَكُنِ ٱللَّهُ لِيَغْفِرَ لَهُمْ وَلَا لِيَهْدِيَهُمْ سَبِيلًۢا ﴿١٣٧﴾ بَشِّرِ ٱلْمُنَٰفِقِينَ بِأَنَّ لَهُمْ عَذَابًا أَلِيمًا ﴿١٣٨﴾ ٱلَّذِينَ يَتَّخِذُونَ ٱلْكَٰفِرِينَ أَوْلِيَآءَ مِن دُونِ ٱلْمُؤْمِنِينَ ۚ أَيَبْتَغُونَ عِندَهُمُ ٱلْعِزَّةَ فَإِنَّ ٱلْعِزَّةَ لِلَّهِ جَمِيعًا ﴿١٣٩﴾ وَقَدْ نَزَّلَ عَلَيْكُمْ فِى ٱلْكِتَٰبِ أَنْ إِذَا سَمِعْتُمْ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ يُكْفَرُ بِهَا وَيُسْتَهْزَأُ بِهَا فَلَا تَقْعُدُواْ مَعَهُمْ حَتَّىٰ يَخُوضُواْ فِى حَدِيثٍ غَيْرِهِۦٓ ۚ إِنَّكُمْ إِذًا مِّثْلُهُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ جَامِعُ ٱلْمُنَٰفِقِينَ وَٱلْكَٰفِرِينَ فِى جَهَنَّمَ جَمِيعًا ﴿١٤٠﴾ ٱلَّذِينَ يَتَرَبَّصُونَ بِكُمْ فَإِن كَانَ لَكُمْ فَتْحٌ مِّنَ ٱللَّهِ قَالُوٓاْ أَلَمْ نَكُن مَّعَكُمْ وَإِن كَانَ لِلْكَٰفِرِينَ نَصِيبٌ قَالُوٓاْ أَلَمْ نَسْتَحْوِذْ عَلَيْكُمْ وَنَمْنَعْكُم مِّنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ۚ فَٱللَّهُ يَحْكُمُ بَيْنَكُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۗ وَلَن يَجْعَلَ ٱللَّهُ لِلْكَٰفِرِينَ عَلَى ٱلْمُؤْمِنِينَ سَبِيلًا ﴿١٤١﴾

**136-141.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በአላህና በመልዕክተኛው በዚያም በመልዕክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ ከዚያም በፊት ባወረደው መፅሐፍ እመኑ። በአላህ፤ በመላዕክቱም በመጽሐፍትም፣ በመልዕክተኞቹና በመጨረሻውም ቀን የካደ ሰው ሁሉ ከእውነት የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ። እነዚያ በነብዩ ሙሳ ያመኑና ከዚያም ወይፈንን በመገዛት የካዱ

ከዚያም (በእርሱ) ያመኑና ከዚያም በዒሳ የካዱ ከዚያም በሙሐመድ ክህደትን የጨመሩ ሰዎች አላህ ለእነርሱ የሚምራቸውና ቅኑን መንገድ የሚመራቸው አይደለም። መናፍቃንን ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት ያላቸው መሆኑን አብስራቸው። እነዚያ ከምዕመናን ሌላ ከሐዲያንን ወዳጆች አድርገው የሚይዙ ሰዎች እነርሱ ዘንድ ልቅናን ይፈልጋሉን? ልቅና ሁሉ ለአላህ ብቻ ነው። በእናንተም ላይ በመጽሐፍ ውስጥ የአላህን አንቀፆች በእርሷ ሲካድባት በእርሷም ሲላገጥባት በሰማችሁ ጊዜ በሌላ ወሬ ውስጥ እስከሚገቡ ከእነርሱ ጋር አትቀመጡ ማለትን በእርግጥ አወረደ። እናንተ ያን ጊዜ ቢጤያቸው ናችሁና። አላህ መናፍቃንንና ከሓዲያንን መላውንም በገሀነም ውስጥ ሰብሳቢ ነውና። መናፍቃን ማለት በእናንተ ላይ የጊዜ መዘዋወርን የሚጠባበቁ ናቸው። ለእናንተም ከአላህ የሆነ አሸናፊነት ቢኖራችሁ ከናንተ ጋር አልነበረምን? ይላሉ። ለከሐዲያን እድል ቢኖር ደግሞ (ከአሁን በፊት) እኛ ከአማኞች ቅጣት አልተከላከልንላችሁምን? ከምዕመናንም አደጋ አልከለከልናችሁምን? ይላሉ። አላህ በትንሳኤ ቀን በመካከላችሁ በትክክል ይፈርዳል። አላህ ለከሐዲያን ሁሉ በምዕመናን ላይ መንገድን በፍፁም አያደርግም።

إِنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ يُخَٰدِعُونَ ٱللَّهَ وَهُوَ خَٰدِعُهُمۡ وَإِذَا قَامُوٓاْ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ قَامُواْ كُسَالَىٰ يُرَآءُونَ ٱلنَّاسَ وَلَا يَذۡكُرُونَ ٱللَّهَ إِلَّا قَلِيلٗا ﴿١٤٢﴾ مُّذَبۡذَبِينَ بَيۡنَ ذَٰلِكَ لَآ إِلَىٰ هَٰٓؤُلَآءِ وَلَآ إِلَىٰ هَٰٓؤُلَآءِۚ وَمَن يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَلَن تَجِدَ لَهُۥ سَبِيلٗا ﴿١٤٣﴾

**142-143.** መናፍቃን አላህን ያታልላሉ። እርሱም አታላያቸው ነው (ይቀጣቸዋል)። መናፍቃን ወደ ሶላት በቆሙ ጊዜ ታካቾች ሰዎችን የሚያሳዩ ሆነው ይቆማሉ። አላህን ጥቂትን እንጂ አያወሱም። በዚህ መካከል ወላዋዮች ሆነው ይታያሉ። ወደ እነዚህም ወደ እነዚያም አይደሉም። አላህ ያሳሳተው ሰው ሁሉ ለእነርሱ የቅንነት መንገድን በፍፁም አታገኝለትም።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُواْ ٱلۡكَٰفِرِينَ أَوۡلِيَآءَ مِن دُونِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَۚ أَتُرِيدُونَ أَن تَجۡعَلُواْ لِلَّهِ عَلَيۡكُمۡ سُلۡطَٰنٗا مُّبِينًا ﴿١٤٤﴾

**144.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከምዕመናን ሌላ ከሐዲያንን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ። ለአላህ በእናንተ ላይ ግልፅ ማስረጃዎችን ልታደርጉ ትፈልጋላችሁን?

إِنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ فِي ٱلدَّرۡكِ ٱلۡأَسۡفَلِ مِنَ ٱلنَّارِ وَلَن تَجِدَ لَهُمۡ نَصِيرًا ١٤٥ إِلَّا ٱلَّذِينَ تَابُواْ وَأَصۡلَحُواْ
وَٱعۡتَصَمُواْ بِٱللَّهِ وَأَخۡلَصُواْ دِينَهُمۡ لِلَّهِ فَأُوْلَٰٓئِكَ مَعَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَۖ وَسَوۡفَ يُؤۡتِ ٱللَّهُ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ
أَجۡرًا عَظِيمٗا ١٤٦ مَّا يَفۡعَلُ ٱللَّهُ بِعَذَابِكُمۡ إِن شَكَرۡتُمۡ وَءَامَنتُمۡۚ وَكَانَ ٱللَّهُ شَاكِرًا عَلِيمٗا ١٤٧

**145-147.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መናፍቃን በእርግጥ ከእሳት በታችኛዋ አዘቅት ውስጥ ናቸው። እናም ለእነርሱ* ረዳትን አታገኝላቸውም። እነዚያ የተመለሱና ስራቸውን ያሳመሩ በአላህ የተጠበቁ ሃይማኖታቸውንም ለአላህ ፍፁም ያደረጉ ሰዎች ሲቀሩ። እነዚያስ ከምዕመናን ጋር ናቸው። ለምዕመናንም አላህ ታላቅን ምንዳ በእርግጥ ይሰጣል። ብታመሰግኑና ብታምኑ አላህ እናንተን በመቅጣት ምን ያደርጋል? አላህም ወረታን መላሽ አዋቂ ነው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የሚከተሉት አራት ባሕሪያት የተንፀባረቁበት ሰውና ከነዚህ አራት ባህሪያት መካከል አንዱ የታየበት ሰው እስኪተዋቸው ድረስ በእርግጥ ከአስመሳዮች ነው»

1. አደራ በእምነት ቢሰጠው የተሰጠውን አደራ ይክዳል።
2. ከተናገረ ይዋሻል፤
3. ቃል ከገባ ቃሉን ያጥፋል፤
4. ከሰዎች ጋር በሚጋጭበት ወቅት ከሐቅ ይሸሻል ይህ ማለት እነዚህ ነገሮች ግን ከእስልምና አያስወጡም።

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በአላህ ፊት ከሰዎች ሁሉ በጣም መጥፎ የሆኑት እነዚያ ሁለት የፊት ገፅታዎች የሏቸው ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ለተወሰኑ ሰዎች አንድ መልክ ሲያሳዮ ለሌሎች ሰዎች ደግሞ ሌላ መልክ የሚያሳዩ ናቸው»

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (135-147) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎች፡-**

1. ፍትህን በመስጠትም ሆነ በምስክርነት ወቅት እውነትን ለመናገር መድፈር ግዴታ መሆኑን እና የሀሰት ምስክርነትን መስጠት እጅግ የተከለከለ ተግባር መሆኑን፤
2. እምነትን መያዝ የአንድ ጊዜ ግዴታ ብቻ ሳይሆን እስከ ህይወት ፍፃሜ ድረስ መተግበር ያለበት መሆኑን፤
3. ከእምነት የወጣ ያፈነገጠ ሙርተድ አድርጎ ወደ እምነቱ እንዲመለስ የሶስት ቀን ጊዜ እንደሚሰጠውና በእነዚህ ቀናት ውስጥ ትልቅ ኃጢአት ውስጥ መግባቱን አምኖ መመለስ እንዳለበት፤
4. ከሓዲያንን መውደድ፤ መጥፎ ሰውን ጓደኛ ማድረግ በኢስላም የተከለከለ መሆኑን፤
5. እንደዚሁ የክህደት የወንጀል ተግባራትን መውደድ በተግባር ኩፍርንና ወንጀልን ከመፈፀም ተለይቶ የማይታይ ድርጊት ነው። አስመሳይነት ከክህደት የባሰ ወንጀል ሲሆን የራሱ መገለጫዎች እንዳሉት፤
6. ለይዩልኝና ለይስሙልኝ መስራት አንዱ የአስመሳዮችነት መገለጫ ሲሆን አስከፊ ወንጀል መሆኑን፤

7. ዚክርን መተውና በጥቂቱ ብቻ አላህን ማስታወስና ማወደሱ የተወገዘ መሆኑን በማወቅ ዘወትር በብዛት ውዳሴና ዚክርን ለአላህ መስጠት እንደሚኖርበት፤
8. ቆራጥነት ውጤታማ ለመሆን የሚያስችል ባህሪ በመሆኑ ቆራጥ መሆንን መልመድ የግድ እንደሆነ በአንፃሩም ወላዋይነት ከብልሹና አላስፈላጊ ባህሪያት እንደሚመደብ ተገንዝቦ ከወላዋይነት መራቅ እንደሚገባ፤
9. ከሓዲያንን መውደድ እጅግ የተከለከለና ሙዕሚኖች የአላህን ጠላቶች ወዳጅ አድርገው በመያዝ ወንጀልን ሲዳፈሩ ጠላቶቻቸውን በላያቸው ላይ እንደሚሾምባቸውና የበታች እንዲሆኑ በማድረግ ምድራዊ ውርደትን እንደሚያከናንባቸው፤
10. ተውበት ከዚህ በፊት የተሰሩ ወንጀሎችን በሙሉ በማሰረዝ ተውባህ አድራጊውን ምንም ወንጀል ያልሰራ ንፁህ ሰው እስከሚሆን ድረስ እንደሚያፀዳው፤
11. የአላህን ፀጋ በማስታወስ የሚያመሰግን አማኝ በሁለቱም ዐለም ቅጣትና መከራ እንደማያጋጥመው እንማራለን።

* لَّا يُحِبُّ ٱللَّهُ ٱلْجَهْرَ بِٱلسُّوٓءِ مِنَ ٱلْقَوْلِ إِلَّا مَن ظُلِمَ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ سَمِيعًا عَلِيمًا ﴿١٤٨﴾

**148.** *አላህ በክፉ ንግግር መጮህን ከተበደለ ሰው ጩኸት በስተቀር አይወድም። አላህ ሰሚና አዋቂ ነውና።

✷ ክፍል ስድስተ

ከሴቶች ምዕራፍ (148) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ሰው በአንድ መንደር እንግድነት ጠይቆ ያስቀይሙትና ስለ ሰዎች ስሞታ በመናገሩ እንደዚህ ሰው የተበደለ ሰው ካልሆነ በቀር ስሞታ መናገር ተገቢ አለመሆኑን ለማስተማር ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ፤ ኢብኑከሲር፤ ኢብኑ-ልጀውዚ እና ሱዩጢ)

إِن تُبْدُوا۟ خَيْرًا أَوْ تُخْفُوهُ أَوْ تَعْفُوا۟ عَن سُوٓءٍ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَفُوًّا قَدِيرًا ﴿١٤٩﴾

**149.** ደግ ነገርን ብትገልፁ ወይም ብትደብቁት ወይም ከመጥፎ ነገር (በደል) ይቅርታ ብታደርጉ አላህ ይቅር ባይ እና ቻይ ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكْفُرُونَ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ وَيُرِيدُونَ أَن يُفَرِّقُوا۟ بَيْنَ ٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ وَيَقُولُونَ
نُؤْمِنُ بِبَعْضٍ وَنَكْفُرُ بِبَعْضٍ وَيُرِيدُونَ أَن يَتَّخِذُوا۟ بَيْنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا ﴿١٥٠﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ
ٱلْكَٰفِرُونَ حَقًّا ۚ وَأَعْتَدْنَا لِلْكَٰفِرِينَ عَذَابًا مُّهِينًا ﴿١٥١﴾ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ وَلَمْ
يُفَرِّقُوا۟ بَيْنَ أَحَدٍ مِّنْهُمْ أُو۟لَٰٓئِكَ سَوْفَ يُؤْتِيهِمْ أُجُورَهُمْ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿١٥٢﴾

**150-152.** እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞቹ የሚክዱ፤ በአላህና በመልዕክተኞቹም መካከል መለየትን የሚፈልጉና በከፊሉም እናምናለን በከፊሉ ደግሞ እንክዳለን የሚሉ ሰዎች ሁሉ በዚህ መካከል መንገድን ሊይዙ

የሚፈልጉ። እነዚያ በእውነቱ ከሐዲያን እነርሱ ናቸው። ለከሐዲያንም አዋራጅን ቅጣት አዘጋጅተናል። እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞቹ ያመኑ ከእነርሱም በአንዱም መካከል ያልለዩ ሰዎች እነዚያ ምንዳዎቻቸው በእርግጥ ይሰጣቸዋል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

يَسۡـَٔلُكَ أَهۡلُ ٱلۡكِتَٰبِ أَن تُنَزِّلَ عَلَيۡهِمۡ كِتَٰبٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِۚ فَقَدۡ سَأَلُواْ مُوسَىٰٓ أَكۡبَرَ مِن
ذَٰلِكَ فَقَالُوٓاْ أَرِنَا ٱللَّهَ جَهۡرَةٗ فَأَخَذَتۡهُمُ ٱلصَّٰعِقَةُ بِظُلۡمِهِمۡۚ ثُمَّ ٱتَّخَذُواْ ٱلۡعِجۡلَ مِنۢ بَعۡدِ مَا
جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَٰتُ فَعَفَوۡنَا عَن ذَٰلِكَۚ وَءَاتَيۡنَا مُوسَىٰ سُلۡطَٰنٗا مُّبِينٗا ١٥٣

**153.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመጽሐፍ ባለቤቶች እነርሱ ላይ ከሰማይ መጽሐፍን እንድታወርድ ይጠይቁሃል። ከዚህ ጥያቄ የከበደን ጥያቄም ከዚህ በፊት ሙሳን በእርግጥ ጠይቀዋል። አላህንም በግልፅ አሳየን ብለዋል። በበደላቸውም ምክንያት መብረቅ ያዘቻቸው። ከዚያም ተዐምራቶች ከመጡላቸው በኋላ ወይፈኑን አምላክ አድረገው ያዙ። ከዚያ ይቅር አልን። ሙሳንም ግልፅ ስልጣን ሰጠነው።

ከሴቶች ምዕራፍ (153) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ካዕብ ቢን አል አሽረፍና የእርሱ ተከታይ የሆኑ አይሁድ ቡድኖች ወደ ነብዩ (ﷺ) ዘንድ መጥተው «አንተ እውነተኛ ነብይ ከሆንክ እንደ ነብዩ ሙሳ አንድ የተጠረዘ መፅሐፍ እስቲ አምጣልን» በማለት ያልሆነ ጥያቄ ሲያቀርቡላቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ፤ ኢብኑል. ጀውዚ እና ሱዩጢ)

وَرَفَعۡنَا فَوۡقَهُمُ ٱلطُّورَ بِمِيثَٰقِهِمۡ وَقُلۡنَا لَهُمُ ٱدۡخُلُواْ ٱلۡبَابَ سُجَّدٗا وَقُلۡنَا لَهُمۡ لَا تَعۡدُواْ فِي
ٱلسَّبۡتِ وَأَخَذۡنَا مِنۡهُم مِّيثَٰقًا غَلِيظٗا ١٥٤ فَبِمَا نَقۡضِهِم مِّيثَٰقَهُمۡ وَكُفۡرِهِم بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ
وَقَتۡلِهِمُ ٱلۡأَنۢبِيَآءَ بِغَيۡرِ حَقّٖ وَقَوۡلِهِمۡ قُلُوبُنَا غُلۡفُۢۚ بَلۡ طَبَعَ ٱللَّهُ عَلَيۡهَا بِكُفۡرِهِمۡ
فَلَا يُؤۡمِنُونَ إِلَّا قَلِيلٗا ١٥٥ وَبِكُفۡرِهِمۡ وَقَوۡلِهِمۡ عَلَىٰ مَرۡيَمَ بُهۡتَٰنًا عَظِيمٗا ١٥٦ وَقَوۡلِهِمۡ إِنَّا
قَتَلۡنَا ٱلۡمَسِيحَ عِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ رَسُولَ ٱللَّهِ وَمَا قَتَلُوهُ وَمَا صَلَبُوهُ وَلَٰكِن شُبِّهَ لَهُمۡۚ
وَإِنَّ ٱلَّذِينَ ٱخۡتَلَفُواْ فِيهِ لَفِي شَكّٖ مِّنۡهُۚ مَا لَهُم بِهِۦ مِنۡ عِلۡمٍ إِلَّا ٱتِّبَاعَ ٱلظَّنِّۚ وَمَا قَتَلُوهُ
يَقِينَۢا ١٥٧ بَل رَّفَعَهُ ٱللَّهُ إِلَيۡهِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمٗا ١٥٨

**154-158.** በቃል ኪዳናቸው ምክንያት የጡር ተራራን ከበላያቸው አነሳን። ለእነርሱም ደጃፍን ስትገቡ አጎንብሳችሁ ግቡ አልን። ለእነርሱም በሰንበት ቀን ትዕዛዝን አትተላለፉ አልን።* ከነርሱም ከባድን ቃል ኪዳን ያዝን።

ቃል ኪዳናቸውን በማፍረሳቸው፤ በአላህ አንቀፆች በመካዳቸው፤ ነብያትን ያለ አግባብ በመግደላቸውና ልቦቻችንም ሽፍኖች ናቸው በማለታቸው ምክንያት (ረገምናቸው)። በእውነቱ በክህደታቸው ምክንያት አላህ በእርሷ ላይ አተመ። ስለዚህ ጥቂትን እንጂ አያምኑም። በመካዳቸውም በመርየም ላይ ከባድ ቅጥፈትን በመናገራቸው ምክንያት (ረገምናቸው)። እኛ የአላህን መልዕክተኛ የመርየም ልጅ አል መሲህ ዒሳን ገደልን በማለታቸውም ረገምናቸው። አልገደሉትም። አልሰቀሉትምም። ግን ለእነርሱ የተገደለ ሰው በዒሳ ተመሰለባቸው። እነዚያ በእርሱ ጉዳይ የተለያዩ ሰዎች በእርሱ መገደል በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ጥርጣሬን ከመከተል በስተቀር በእርሱ ነገር ምንም እርግጠኛ እውቀት የላቸውም። በእርግጥም አልገደሉትም። ይልቁንስ አላህ ወደ እርሱ (ዒሳን) አነሳው። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ «ለእስራኤላዊያን ሰዎች በከተማይቱ በር ፊታችሁን ወደ መሬት ደፍታችሁ ግቡ።«ተፀፀትን» በሉም»ተባሉ። ነገር ግን ቃሉን ለውጠውት። በመቀመጫዎቻቸው እየተሳቡ ወደ ከተማዋ ገቡ። «የስንዴ ፍሬ በፀጉር ውስጥ» አሉም» የስንዴ ፍሬ በፀጉር ውስጥ ያሉት የአላህን ትዕዛዝ በቅን መንፈስ ላለመታዘዝ ያላቸውን ፅኑ አቋም ለመግለፅ ነበር። በዚህም ሳቢያ አላህ በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ቅጣቶችን የላከባቸው ሲሆን ከዚህም ውስጥ በተለይ የወረርሽኝ በሽታ መቅሰፍት እንደትልቅ ምሳሌ ተደርጎ ይወስዳል። (ተፍሲር አጥጦበሪ)

وَإِن مِّنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ إِلَّا لَيُؤۡمِنَنَّ بِهِۦ قَبۡلَ مَوۡتِهِۦۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَكُونُ عَلَيۡهِمۡ
شَهِيدٗا ١٥٩ فَبِظُلۡمٖ مِّنَ ٱلَّذِينَ هَادُواْ حَرَّمۡنَا عَلَيۡهِمۡ طَيِّبَٰتٍ أُحِلَّتۡ لَهُمۡ وَبِصَدِّهِمۡ عَن
سَبِيلِ ٱللَّهِ كَثِيرٗا ١٦٠ وَأَخۡذِهِمُ ٱلرِّبَوٰاْ وَقَدۡ نُهُواْ عَنۡهُ وَأَكۡلِهِمۡ أَمۡوَٰلَ ٱلنَّاسِ بِٱلۡبَٰطِلِۚ
وَأَعۡتَدۡنَا لِلۡكَٰفِرِينَ مِنۡهُمۡ عَذَابًا أَلِيمٗا ١٦١

**159-161.** ከመጽሐፍት ባለቤቶች መካከል ከነብዩ ዒሳ ሞት በፊት በነብዩ ዒሳ በእርግጥ በትክክል የሚያምን እንጂ አንድም የለም። በትንሳኤ ቀንም (ዒሳ) በእነርሱ ላይ መስካሪ ይሆናል። ከእነዚያ ከአይሁዳውያን መካከል በፈፀሙት በደልና ሰዎችን ከአላህ መንገድ በብዙ በመከልከላቸው ምክንያት ለእነርሱ ተፈቅደው የነበሩትን ጣፋጮች ምግቦች እርም አደረግንባቸው። ከእርሱ በቁርጥ የተከለከሉ ሲሆኑ አራጣን በመያዛቸውና የሰዎችን ገንዘቦች ያለ አግባቡ በመብላታቸውም ምክንያት የተፈቀደላቸውን እርም አደረግንባቸው። ከእነርሱም መካከል ለከሐዲያን አሳማሚ ቅጣት አዘጋጀን።

لَّٰكِنِ ٱلرَّٰسِخُونَ فِي ٱلۡعِلۡمِ مِنۡهُمۡ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَ يُؤۡمِنُونَ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ
وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبۡلِكَۚ وَٱلۡمُقِيمِينَ ٱلصَّلَوٰةَۚ وَٱلۡمُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ
وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ أُوْلَٰٓئِكَ سَنُؤۡتِيهِمۡ أَجۡرًا عَظِيمًا ﴿١٦٢﴾

**162.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ግን ከእነርሱ ውስጥ በእውቀት የጠለቁት ክፍሎችና ትክክለኛ ምዕመናኖቹ በአንተ ላይ በተወረደውና ከአንተ በፊት በተወረደው መጽሐፍ የሚያምኑ ሲሆኑ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው ሰጋጆችን (እናመሰግናለን)። ዘካንም ሰጪዎቹ በአላህና በመጨረሻው ቀን አማኞች እነዚያ ታላቅ ምንዳን በእርግጥ እንሰጣቸዋለን።*

✳ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሥራዎች የሚመዘኑበት በልብ ውሳኔ (ኒያ) ነው። ማንኛውም ሰው ያሰበውን ያገኛል። ስደቱ ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው ከሆነ፤ ስደቱ ወደ አላህና መልዕክተኛው ነው። የተሰደደው አለማዊ ጥቅምን ለማግኘት ወይም አንዲትን ሴት ለማግባት ከሆነ ስደቱ ለተሰደደበት ነገር ነው»

*إِنَّآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ كَمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ نُوحٖ وَٱلنَّبِيِّـۧنَ مِنۢ بَعۡدِهِۦۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ
وَإِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَٱلۡأَسۡبَاطِ وَعِيسَىٰ وَأَيُّوبَ وَيُونُسَ وَهَٰرُونَ وَسُلَيۡمَٰنَۚ
وَءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ زَبُورٗا ﴿١٦٣﴾ وَرُسُلٗا قَدۡ قَصَصۡنَٰهُمۡ عَلَيۡكَ مِن قَبۡلُ وَرُسُلٗا لَّمۡ نَقۡصُصۡهُمۡ
عَلَيۡكَۚ وَكَلَّمَ ٱللَّهُ مُوسَىٰ تَكۡلِيمٗا ﴿١٦٤﴾ رُّسُلٗا مُّبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَ لِئَلَّا يَكُونَ لِلنَّاسِ عَلَى
ٱللَّهِ حُجَّةُۢ بَعۡدَ ٱلرُّسُلِۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمٗا ﴿١٦٥﴾

**163-165.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ወደ ኑህና ከእርሱ በኋላ ወደ ነበሩት ነብያት መልዕክታችንን እንዳወረድን ሁሉ ወደ አንተም ቁርአንን አወረድን።* ወደ ነብዩ ኢብራሂምም ወደ ነብዩ ኢስማኢልም ወደ ነብዩ ኢስሃቅም ወደ ነብዩ የዕቆብም ወደ ነገዶችም ወደ ነብዩ ኢሳም ወደ ነብዩ አዩብም ወደ ነብዩ ዩኑስም ወደ ነብዩ ሃሩንና ወደ ነብዩ ሱለይማን አወረድን። ለነብዩ ዳውድም ዘቡርን ሰጠነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዚህም በፊት በአንተ ላይ በእርግጥ የተረክንላቸውን መልዕክተኞች በአንተ ላይም ያልተረክንላቸውንም መልዕክተኞች እንደላክን ሁሉ አንተን ላክንህ። አላህ ነብዩ ሙሳንም ማነጋገርን አነጋገረው። ከመልዕክተኞች በኋላ ለሰዎች በአላህ ላይ ምንም አስረጂ እንዳይኖራቸው አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች አድርገን መልዕክተኞችን ላክን። አላህ አሸናፊ፤ ጥበበኛ ነውና።

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የምእመናን እናት የሆኑት ዓኢሻህ እንዳስተላለፉት አል. ሐሪስ የተባለው ሶሐብይ ነብዩን «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ወሕይ እንዴት ነው የሚመጣልዎት?» ሲል ጠየቃቸው። እሳቸውም «አንዳንድ ጊዜ ልክ እንደ ደውል ድምፅ ሆኖ ይመጣልኛል» ይህ አይነቱ ወሕይ ከሁሉም በላይ በጣም ከባዱ ነበር። አሁን ወሕይ ምን መሆኑን ካወቅኩ በኋላ ትቶኛል። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ መልአኩ በሰው ተመስሎ ወደኔ በመምጣት ያናግረኛል። እኔም ያለውን ሁሉ እረዳለሁ» ብለዋል። ዓኢሻህ ይህን አስመልክተው ሲናገሩ «በእርግጥ በጣም ብርዳማ በሆነ ቀን ወሕይ ሲመጣባቸው ነብዩ በዚያ ብርዳማ ቀን ከግንባራቸው ላብ ሲወርድ ተመልክቻለሁ» ብለዋል።

لَّٰكِنِ ٱللَّهُ يَشْهَدُ بِمَآ أَنزَلَ إِلَيْكَ ۖ أَنزَلَهُۥ بِعِلْمِهِۦ ۖ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ يَشْهَدُونَ ۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدًا ﴿١٦٦﴾

**166.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ግን አላህ በአንተ ላይ ባወረደው ቁርኣን ይመሰክራል። በእውቀቱ አወረደው። መላዕክቱም ይመሰክራሉ። መስካሪነትም በአላህ ብቻ በቃ።

ከሴቶች ምዕራፍ (166) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የመካ አስተዳዳሪዎች ወደ ነብዩ በመምጣት «አይሁዶችን ስለ አንተ በመፅሐፋቸው ተጠቅሶ ከሆነ እንዲነገሩን ጠይቀን ምንም እንደማያውቁ በመፅሐፍቸውም እንዳልተወሳህ ነው የነገሩን። ስለ አንተ ምንነት የሚመሰክር ማን አለ?» በማለት እየጠየቋቸው ባሉበት የሆኑ አይሁዶች ባጠገባቸው ሲያልፉ ነብዩ «ወላሂ የአላህ መልክተኛ መሆኔን ታውቃላችሁ» ሲሏቸው አይሁዶች በአንድ አፍ «ወላሂ አናውቅም» ስላሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ ኢብኑ ከሲር፣ ኢብኑል. ጀውዚ እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَصَدُّوا۟ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ قَدْ ضَلُّوا۟ ضَلَٰلًۢا بَعِيدًا ﴿١٦٧﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟
وَظَلَمُوا۟ لَمْ يَكُنِ ٱللَّهُ لِيَغْفِرَ لَهُمْ وَلَا لِيَهْدِيَهُمْ طَرِيقًا ﴿١٦٨﴾ إِلَّا طَرِيقَ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَآ
أَبَدًا ۚ وَكَانَ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرًا ﴿١٦٩﴾

**167-169.** እነዚያ በአላህ የካዱና ከአላህ መንገድም ሰዎችን ያገዱ ሰዎች ከእውነት የራቀን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳቱ። እነዚያ በአላህ የካዱና ሰዎችን የበደሉ ሰዎች አላህ የሚይምራቸውና ቅን መንገድን የሚመራቸው አይደለም። ግን በውስጧ ለዘልዓለም ዘወታሪዎች ሲሆኑ የገሀነምን መንገድ ይመራቸዋል። ይህ ተግባር በአላህ ላይ ገር ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدْ جَآءَكُمُ ٱلرَّسُولُ بِٱلْحَقِّ مِن رَّبِّكُمْ فَـَٔامِنُوا۟ خَيْرًا لَّكُمْ ۚ
وَإِن تَكْفُرُوا۟ فَإِنَّ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا ﴿١٧٠﴾

**170.** እናንተ ሰዎች ሆይ! መልዕክተኛው እውነትን ከጌታችሁ አመጣላችሁ። እናም እመኑም። በሱ ማመናችሁ ለእናንተ የተሻለ ይሆናል። በአላህ ብትክዱም እሱን ቅንጣት ያክል አትጎዱትም። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነውና። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው።

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (148-170) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎች፡-**

1. ስሞታን ለማሰማት አቤቱታን ለማቅረብ ካልሆነ በስተቀር ወንጀልን ይፋ አድርጎ መናገር የተከለከለ መሆኑን፤
2. መልካም ስራን በይፋም ሆነ በድብቅ በግልፅም ሆነ በሚስጥር መተግበሩ ተወዳጅ መሆኑን፤
3. አንድ ሙስሊም ለሙዕሚን ወንድሙ ጥፋቱን በይቅርታ ማለፍ ተገቢ መሆኑን፤
4. የአይሁድ ክህደት ከክርስቲያኖች የክህደት ደረጃ ላቅ ያለ መሆኑን፤
5. ከአላህና ከረሱል ድንጋጌዎች ውስጥ አንዱን እንኳ ያስተባበለ ከሃዲ እንደሚባል፤
6. በከፊል ነብያትን አምኖ ከፊሉን መካድ ከእምነት አጥር የሚያወጣ የክህደት ተግባር መሆኑን፤
7. ከኢስላም ውጪ ያሉ ሀይማኖቶች አመለካከቶችና ፍልስፍናዎች ሁሉ መጨረሻቸው ኪሳራና ፋይዳ ቢስ ድካም መሆኑን፤
8. ነብያት ወደዚች ምድር የመላካቸው አብይ አላማና ምክንያት ህዝቡን ከኩፍር ወደ እምነት ማምጣትመሆኑን፤
9. ተናጋሪነት ከአላህ መልካም ባህሪያት የሚመደብ መሆኑን፤
10. ስለ ነብዩ አላህ እና መላዕክቶች የምስክርነት ቃል የሰጡ መሆናቸዉን፤
11. ቁርአን የሰው ልጅ ተግባራዊ ሊያደርጋቸው የሚገቡ ህግጋትና ስርዓቶችን ያካተተ የተከበረ መፅሐፍ መሆኑን፤
12. አይሁድ የኢስላምን እውነተኛነት የሚያውቁና በትዕቢት ከእውነታ ያፈነገጡ ቃል የማይጠብቁ ቃል አባዮች መሆናቸዉን፤
13. እንዲሁም ክርስቲያኖች ዒሳ ተሰቅሏል ሞቷል በማለት የሚነዙት ወሬ ፍፁም ውሸት መሆኑን፤
14. ነብዮላህ ዒሳ ያልሞቱና ወደ ሰማይ ያረጉ መሆናቸውን፤
15. ነብዩላህ ዒሳ ወደ ሰማይ ቢያርጉም በመጨረሻው ዘመን ወደ ምድር ተመልሰው በመምጣት በምድር ላይ ቆይታ ካደረጉ በኋላ እንደ ማንኛውም ሰው ሞትን እንደሚቀምሱ፤
16. የአላህን ቅጣት መኖሩን በአይን በመመልከት ወደ እምነት መመለሱ ተቀባይነት እንደሌለው፤
17. ወንጀል በምድራዊ ህይወትም ሆነ በአኼራ ሕይወት የአላህ ፀጋዎችን ከማግኘት የሚያግድና የሚያስከለክል መሆኑን፤
18. መጥፎ አርአያ በመሆን ሰዎች ወደ አላህ ዲን እንዳይገቡ እንቅፋት መሆን የተከለከለ መሆኑን፤
19. ወለድ የተከለከለና የተወገዘ ባህሪ ከመሆኑም ባሻገር ለአኼራ ቅጣት የሚጋብዝ ከባድ ወንጀል መሆኑን፤
20. የሰዎችን ንብረትና ገንዘብ ያለ አግባብ መውሰድ ክልክል መሆኑን፤
21. ከአይሁድ ምሁራን መካከል ጥቂት መልካም ሰዎች እንደነበሩ፤
22. ጥልቅና ሰፊ የሆነ ትክክለኛ እምነት ከብዙ ስህተቶች የሚጠብቅ ጋሻ መሆኑን፤
23. ሰላም ከመሰረታዊ የኢስላም ተግባራት ዋነኛ መሆኑንና ታላቅ ምንዳ እንደሚያስገኝ፤
24. ነብዩ ከአላህ በመላክ የመጀመሪያ ነብይ እንዳልሆኑ፤

25. ነብዩ የወረደው መልዕክት ለሌሎችም ነብያት የወረደው አይነት መሆኑን'
26. የሁሉም ነብያት ተልዕኮ ምን እንደነበር፤
27. ከክህደቶች ሁሉ የሚከፋው የራስ ሳይበቃ ሌላውን ሰው እምነትን እንዳይቀበል እንቅፋት የመሆን ክህደት መሆኑን፤
28. ሰው ከዕለት ወደ ዕለት ወንጀሉ እየበዛና በወንጀል እየተዘፈቀ ሲሄድ ተውበት የማድረግ እድሉ እየመነመነ ይመጣል።
29. የታላቁ ነብዩ መልዕክተኛነት ለተወሰኑ ህዝቦች በቻ ሳይሆን ለመላው የሰው ዘር በሙሉ መሆኑን፤
30. አላህ እውቀቱ የሰፋና ጥልቅ ያለው መሆኑን፤ ጥበቡም እንዲሁ ረቂቅ የሆነ ጌታ መሆኑን እንማራለን።

يَـٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَـٰبِ لَا تَغۡلُواْ فِي دِينِكُمۡ وَلَا تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ إِلَّا ٱلۡحَقَّۚ إِنَّمَا ٱلۡمَسِيحُ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ رَسُولُ ٱللَّهِ وَكَلِمَتُهُۥٓ أَلۡقَىٰهَآ إِلَىٰ مَرۡيَمَ وَرُوحٞ مِّنۡهُۖ فَـَٔامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦۖ وَلَا تَقُولُواْ ثَلَٰثَةٌۚ ٱنتَهُواْ خَيۡرٗا لَّكُمۡۚ إِنَّمَا ٱللَّهُ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ سُبۡحَٰنَهُۥٓ أَن يَكُونَ لَهُۥ وَلَدٞۘ لَّهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَكِيلٗا ١٧١

**171.** እናንተ የመጽሐፍ ባለቤቶች ሆይ! በሃይማኖታችሁ ወሰንን አትለፉ።*1 በአላህም ላይ እውነትን እንጂ አትናገሩ። የመርየም ልጅ አል መሲህ ዒሳ የአላህ መልዕክተኛ ወደ መርየም የጣላት የሁን ቃሉና ከእርሱ የሆነ መንፈስ ብቻ ነው። በአላህና በሁሉም በመልክተኞችም እመኑ። አማልዕክት ሶስት ናቸው አትበሉ። ተከልከሉ። ለእናንተ የተሻለ ይሆናልና። አላህ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ለእርሱ ልጅ ያለው ከመሆን የጠራ ነው። በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ የእርሱ ነው። መመኪያነትም በአላህ በቃ።*2

*1 በማጋነን ወሰንን ማለፍ ከሚገባው በላይ ማዕረግ መስጠት ማለት ነው። ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተገቢው በላይ እንዳጋነኑት እኔንም ከተገቢው በላይ አታጋኑኝ። እኔ የአላህ አገልጋይ ነኝ። እናም«የአላህ አገልጋይና መልዕክተኛ በሉኝ» ብለዋል። እንደዚሁም ከነብዩ በተዘገበው ሐዲስ (ማጋነንን ተጠንቀቁ። ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ለጥፋት የዳረጋቸው አጉል ማጋነን ነበርና» ብለዋል።

*2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ማንኛውም ሰው ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም፤ ሙሐመድም ባሪያውና መልዕክተኛው ናቸው። ዒሳ የአላህ ባሪያ፤ መልዕክተኛና በመርየም ማህፀን ውስጥ በቃሉ የተፈጠረ መሆኑን፤ ጀነትም ሐቅ ነች፤ ጀሀነምም ሐቅ ነች ብሎ የመሰከረ ሰው የሰራው ስራ ምንም ኢምንት ቢሆን አላህ በሰራው ስራ ጀነት እንዲገባ ያደርገዋል።»

لَّن يَسْتَنكِفَ ٱلْمَسِيحُ أَن يَكُونَ عَبْدًا لِّلَّهِ وَلَا ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ ٱلْمُقَرَّبُونَ ۚ وَمَن يَسْتَنكِفْ عَنْ
عِبَادَتِهِۦ وَيَسْتَكْبِرْ فَسَيَحْشُرُهُمْ إِلَيْهِ جَمِيعًا ﴿١٧٢﴾ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ
فَيُوَفِّيهِمْ أُجُورَهُمْ وَيَزِيدُهُم مِّن فَضْلِهِۦ ۖ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ ٱسْتَنكَفُوا۟ وَٱسْتَكْبَرُوا۟ فَيُعَذِّبُهُمْ
عَذَابًا أَلِيمًا وَلَا يَجِدُونَ لَهُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَلِيًّا وَلَا نَصِيرًا ﴿١٧٣﴾

**172-173.** አል መሲህ ለአላህ ባሪያ ከመሆን ፈፅሞ አይጠየፍም። ቀራቢዎች የሆኑ መልዐክትም እንዲሁ ለአላህ ባሪያ ከመሆን ፈፅሞ (አይጠየፉም)። ወደ አላህ እርሱን ከመገዛት የሚፀየፉና የሚኮሩ ሰዎች ሁሉ አላህ ሁሉንም ወደ እርሱ በእርግጥ ይሰበስባቸዋል። እነዚያማ በአላህ ያመኑና መልካም ተግባራትን የሰሩ ሰዎች ሁሉ ምንዳዎቻቸውን ይሞላላቸዋል። ከችሮታውም ይጨምርላቸዋል። እነዚያን የተፀየፉትና የኮሩትን ሰዎች አሳማሚውን ቅጣት ይቀጣቸዋል። ከአላህ ሌላ ለእነርሱ ዘመድንና ረዳትን አያገኙም።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدْ جَآءَكُم بُرْهَٰنٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَأَنزَلْنَآ إِلَيْكُمْ نُورًا مُّبِينًا ﴿١٧٤﴾
فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَٱعْتَصَمُوا۟ بِهِۦ فَسَيُدْخِلُهُمْ فِى رَحْمَةٍ مِّنْهُ وَفَضْلٍ
وَيَهْدِيهِمْ إِلَيْهِ صِرَٰطًا مُّسْتَقِيمًا ﴿١٧٥﴾

**174-175.** እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ዘንድ በእርግጥም አስረጅ መጣላችሁ። ወደ እናንተም ገለጭ የሆነን ብርሃንን ቁርአን አወረድን። እነዚያማ በአላህ ያመኑና በእርሱ የተጠበቁ ሰዎች ከእርሱ በሆነው እዝነትና ችሮታ ውስጥ እርግጥ ያስገባቸዋል። ወደ እርሱም ቀጥተኛ መንገድ ይመሯቸዋል።

يَسْتَفْتُونَكَ قُلِ ٱللَّهُ يُفْتِيكُمْ فِى ٱلْكَلَٰلَةِ ۚ إِنِ ٱمْرُؤٌا۟ هَلَكَ لَيْسَ لَهُۥ وَلَدٌ وَلَهُۥٓ أُخْتٌ فَلَهَا
نِصْفُ مَا تَرَكَ ۚ وَهُوَ يَرِثُهَآ إِن لَّمْ يَكُن لَّهَا وَلَدٌ ۚ فَإِن كَانَتَا ٱثْنَتَيْنِ فَلَهُمَا ٱلثُّلُثَانِ مِمَّا تَرَكَ ۚ
وَإِن كَانُوٓا۟ إِخْوَةً رِّجَالًا وَنِسَآءً فَلِلذَّكَرِ مِثْلُ حَظِّ ٱلْأُنثَيَيْنِ ۗ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمْ أَن تَضِلُّوا۟ ۗ
وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌۢ ﴿١٧٦﴾

**176.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይጠይቁሃል። ወላጆችና ልጅ ሳይኖረው በሚወረስ ሟች ሰው ጉዳይ አላህ ይነግራችኋል። ልጅ የሌለው ሰው ቢሞትና ለእርሱ እህት ብትኖረው ለእርሷ ከተወው ንብረት ግማሽ አላት። እርሱም ለእርሷ ልጅ የሌላት እንደሆነች (በሙሉ) ይወርሳታል። ሁለት

# እህቶች ወይም ከሁለት በላይ ቢሆኑም ከተወው ንብረት ከሶስት ሁለት እጅ አላቸው፡፡ ወንድሞችና (እህቶች) ወንዶችና ሴቶች ቢሆኑም ለወንድ የሁለት ሴቶች ድርሻ ያህል አለው፡፡ አላህ እንዳትሳሳቱ ለእናንተ ያብራራል፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ አዋቂ ነው በላቸው፡፡*

* ይህ አንቀፅ በመጨረሻ የወረደ አንቀፅ ነው ተብሏል፡፡ ቡኻሪ «መጨረሻ የወረደው በራአቱ ሲሆን የመጨረሻው አንቀፅ ደግሞ ይህ አንቀፅ ነው» ብለዋል፡፡

ከሴቶች ምዕራፍ (176) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክያንያት፡- ጃቢር ቢን ዐብዱላህ እንዳሉት «ነብዩ (ﷺ) ታምሜ እያለሁ ሊያዩኝ መጡና ፊቴ ላይ ዱዓ ቀርተው ተፉልኝ ትንሽም ቀለል አለኝ፡፡ ተነስቼ ቁጭ አልኩ፡፡ ሰባት እህቶች ነበሩኝና የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለእናቴ ልጆች ለእህቶቼና ለወንድሞቼ ሁለት ሶስተኛ ገንዘቤን ልናዘዝላቸው በማለት ስጠይቃቸው ከዚህም ቀንስ አሉኝ፡፡ አንድ ሶስተኛስ ስላቸው እሱም ብዙ ነው ብለውኝ ወጥተው ሄዱ፡፡ ከዚያም ተመልሰው በመምጣት ጃቢር ሆይ! በዚህ ህመምህ የምትሞት አይመስለኝም፡፡ ስለ እህቶችህ ግን አላህ (⅔) እንደሚገባቸው ቁርኣን አውርዷል በማለት ይህ አንቀፅ በእነርሱ ምክንያት እንደወረደ ዘግቧል፡፡ (አቡ ዳውድ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከሴቶች ምዕራፍ ከአንቀፅ (171-176) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎች፡-**

1. ነገርን ባለው ደረጃ ማቅረብና ማውራት እንጂ ማጋጋልና መጨማመር ውሸት በመሆኑ የተከለከለ መሆኑን፤
2. ያለ በቂ እውቀት በአላህ ላይ መናገር የተከለከለ መሆኑን፤
3. ነብዩ ዒሳ ትክክለኛውን እምነት የያዙና ይህንንም ለህዝባቸው ለማስተማር ከአላህ የተላኩ መልዕክተኛ እንደነበሩ፤
4. እውነትን ያለመቀበል ከኩራት የሚመደብ የተወገዘ ባህሪ እንደሆነ፤
5. አኼራን በተመለከተ መጠነኛ ዝርዝር ጉዳዩች፤
6. የኢስላም ጥሪ ለሁሉም የመጣ በመሆኑ የሰው ዘር በሙሉ ጥሪው የሚመለከተው እንደሆነ፤
7. ቁርኣን ሀቅን ፍንትው አድርጎ የሚያሳይ የሕይወት ብርሀን መሆኑን፤
8. ትክክለኛ እምነት ጀነትን የሚያሸልምና ጀነትን የሚገዛ መሆኑን፤
9. እውቀት የሌለው ሰው ሁሉ እውቀት ያለውን በመጠየቅ ስለማንኛውም ጉዳይ ግንዛቤ መያዝና መረዳት የሚችል መሆኑን፤
10. ልጅም የልጅ ልጅም ሳይኖረው የሞተ ሰው ዉርሱ እንዴት መወረስ እዳለበት እንማራለን፡፡

## በአላህ ፈቃድ የሴቶች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ፡፡

# ምዕራፍ (5)
# የማዕዱ ምዕራፍ
# (ሱረቱ አልማእዳህ)

سُورَةُ المَائِدَةِ

## የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ (120) ናቸው።
## የሱረቱ አል ማኢዳህ መግቢያ

በዉስጡ የተወሱት ህግጋት ሁሉ የተሻረ የለባቸዉም። በዉስጡ በሌሎች ምእራፎች ዉስጥ ያልተወሱ ነገሮች ሁሉ አሉበት። በዉስጡ ከተጠቀሱት ህግጋት መካከል:- በቃል ኪዳን ላይ መገኘት ግዴታ መሆኑን፤ ከምግቦች መካከል ከተከለከሉት ነገሮች የተወሰኑትን አውስቶ፤ የተፈቀዱትን ምግቦች፤ የመፅሐፍ ባለቤት ሴትን የሙስሊም ወንድ ማግባት እንደተፈቀደለት፤ የውዱእን ግዴታዎች፤ የተይሙምን ስርዓት፤ ፍትህ ከጠላትም ጋር ቢሆንም አስፈላጊ መሆኑን፤ አላህ ለሙስሊሞች የዋለላቸውን ፀጋ ማስታወስና መፅሐፋቸውን መጠበቅ ግዴታ መሆኑንም ያመለክታል። የሽፍታንና የሌባን ቅጣት ድንጋጌ፤ አይሁድ የተውራትን ሕግ እንዴት እንደጣሱ፤ በሰፊው ይተነትናል። በአላህ ሕግ ሥር መተዳደርም ግዴታ መሆኑን በተደጋጋሚ ያስተምራል።

ምዕራፍ በዘመኑ ያሉት አይሁድና ነሷራ ለሙዕሚኖች ጠላት እንደሆኑና ለእነሱ ማጐብደድ ተገቢ እንዳልሆነ፤ ተግባራቸውን መቃወም እንደሚገባን ያመለክታል። አላህ የሶስቱ ስላሴዎች አንድ ሶስተኛ ነው የሚሉት ወገኖች በብቸኝነቱ ከሃዲ መሆናቸውን አረጋግጦ እውነትን የተቀበሉ ክፍሎች ከፍተኛ ምንዳ እንዳላቸውም በግልፅ አስቀምጧል።

ከዚያ አንዳንድ አማኞች አንዳንድ ነገሮችን በራሳቸው ላይ ክልክል ማድረግ እንደሌለባቸው፤ የማለ ሰው ሲያፈርስ ምን ማድረግ እንዳለበት፤ ኸምር በቁርጥ መከልከሉን፤ የሐጅን ሥርዓት የመካን ክብር የተከለከሉ ወሮችን ክብር ዓረቦች በራሳቸው አነሳሽነት የከለከሏቸውን ነገሮች አላግባብ መሆኑን፤ በመንገድ ላይ አደራ ማለት ተገቢ መሆኑን አውስቶ በነብዩ ዒሳ አማካኝነት የታዩትን ተዓምርና ይህንንም ተመልክተው በኒ ኢስራኢሎች እንዳልተቀበሏቸው፤ በነብዩ ዒሳ አማካኝነት የታዩትን ተዓምራትና ይህንም ተመልክተው በኒ ኢስራኢሎች እንዳልተቀበሏቸው፤ ነብዩ ዒሳ የአመለኳቸውን ሰዎች እንደማያውቋቸው አስታውሶ አላህ የሰማያትና የምድር ንጉስ መሆኑን በማውሳት መልዕክቱን ይደመድማል።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ እናታችን አዒሻ እንዳወሩት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- “ማንም ሰው በዚህ ጉዳያችን -በኢስላም- ከርሱ ያልሆነን አዲስ ነገር ካመጣ፤ አዲሱ ነገር ውድቅ ነው። ”ይህንኑ ሐዲስ ሙስሊም ለየት ባለ መልኩ አስቀምጠውታል:- “የእኛ ትዕዛዝ የሌለበትን ድርጊት የሰራ ስራው ውድቅ ነው»

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَوۡفُواْ بِٱلۡعُقُودِۚ أُحِلَّتۡ لَكُم بَهِيمَةُ ٱلۡأَنۡعَٰمِ إِلَّا مَا يُتۡلَىٰ عَلَيۡكُمۡ غَيۡرَ
مُحِلِّي ٱلصَّيۡدِ وَأَنتُمۡ حُرُمٌۗ إِنَّ ٱللَّهَ يَحۡكُمُ مَا يُرِيدُ ١

**1.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ቃልኪዳኖቻችሁን ሙሉ። በእናንተ ላይ የሚነበበው ብቻ ሲቀር የግመል፣ የዳልጋ ከብት፣ የበግና የፍየል እንስሳት ተፈቅዶላችኋል። በሐጅ ስራ ላይ ሆናችሁ ማደንን እንደ ተፈቀደ ሳትቆጥሩ የሚበሉት የዱር እንስሳትም ተፈቅደውላችኋል። አላህ የሚፈልገውን ሁሉ ነገር ይፈርዳልና።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُحِلُّواْ شَعَٰٓئِرَ ٱللَّهِ وَلَا ٱلشَّهۡرَ ٱلۡحَرَامَ وَلَا ٱلۡهَدۡيَ وَلَا ٱلۡقَلَٰٓئِدَ
وَلَآ ءَآمِّينَ ٱلۡبَيۡتَ ٱلۡحَرَامَ يَبۡتَغُونَ فَضۡلٗا مِّن رَّبِّهِمۡ وَرِضۡوَٰنٗاۚ وَإِذَا حَلَلۡتُمۡ فَٱصۡطَادُواْۚ
وَلَا يَجۡرِمَنَّكُمۡ شَنَـَٔانُ قَوۡمٍ أَن صَدُّوكُمۡ عَنِ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ أَن تَعۡتَدُواْۘ وَتَعَاوَنُواْ عَلَى
ٱلۡبِرِّ وَٱلتَّقۡوَىٰۖ وَلَا تَعَاوَنُواْ عَلَى ٱلۡإِثۡمِ وَٱلۡعُدۡوَٰنِۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۖ إِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ٢

**2.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህ ምልክቶች ይሆኑ ዘንድ የከለከላቸውን ነገሮች ሁሉ የተፈቀዱ አታድርጉ። (አላህ የዲን ምልክት ያደረገቸውን ነገሮች እንደፈለጋችሁ አትሁኑባቸው)። የተከበረውንም ወር በውስጡ ጦርነትን በማካሄድ አትድፈሩት። ወደ መካ የሚነዱትን የመስዋዕት እንስሳትና የሚታበቱባቸውን ገመዶች ከጌታቸው ችሮታንና ውዴታን ፈልገው ወደ ተከበረው ቤት አሳቢዎችንም ሰዎች በክፉ አትንኳቸው። የሐጅን ስራ ፈፅማችሁ በአጠናቀቃችሁ ጊዜ የዱር አውሬዎችን እንደልባችሁ አድኑ። ከተከበረው መስጊድ ስለከለከሏችሁ ሰዎችን መጥላታችሁ በእነርሱ ላይ ወሰንን እንድታልፉና (ፍትህን እንድታዛቡ) አይገፋፋችሁ። በበጎ ተግባር አላህን በመፍራት እርስ በእርስ ተባበሩ። ኃጢአትና ወሰንን በማለፍ ግን አትተባበሩ። አላህን በትክክል ፍሩ። አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና።

ከመዕዱ ምዕራፍ (2) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ሹረይህ ዱበይዕልኪንዲ የተባለ ሰው ከየማማ ወደ መዲና መጥቶ ፈረሱን ከመዲና ውጭ ትቶ ወደ ነብዩ (ﷺ) ገባና ሰዎችን ወደ ምን ነው የምትጠራው? በማለት ጠየቃቸው። ነብዩም (ﷺ) አንድ አላህን ወደ ማምለክ፣ ሶላት

*ወደ መስገድ፤ ዘካን ወደ መስጠት በማለት ነገሩት። እሱም፡- ነገሩ በጣም ጥሩ ነው። ነገር ግን ያለ እነርሱ ምንም ማድረግ የማንችል ኃላፊዎች አሉ። ምን አልባትም ሰልሜ እነሱንም ይዣቸው ልመጣ እችል ይሆናል አላቸው። ነብዩ (ﷺ) ይህ ሰው ከመምጣቱ በፊት በሰይጣን አንደበት የሚናገር ሰው ይመጣባችኋል ብለው ለባልደረቦቻቸው ተናግረው ነበርና ሲወጣ ይህ ሰው በከሐዲ ፊት ገብቶ በአታላይ እግር ወጣ። ሰውየውም ሙስሊም አይደለም አሉ። ሰውየውም እንዳሉትም ወደ ሀገሩ ሲመለስ የመዲናን ግመሎች ሰርቆ ሄደ። ሲፈለግ ጠፍቶ በሰባተኛው ዓመት ዑምራ ለማድረግ ነብዩ (ﷺ) ወደ መካ ሲሄዱ የየማማዎችን የንግድ ቡድን መኖራቸውን ስለሰሙ ነብዩ (ﷺ) ይኸው ያ ሰውየ እና ባልደረቦቹ ናቸው አሉ። ሙስሊሞች እነሱን ለማሳደድ ሲንቀሳቀሱ ይህ አንቀፅ ወረደና ለሐጅ ዝግጅት ያደረጉ ሰዎች ሙስሊሞች ባይሆኑም እንኳን በክፉ ማሰብ እንደማይፈቀድ አስተማራቸው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑል. ጀውዚ፤ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)*

حُرِّمَتۡ عَلَيۡكُمُ ٱلۡمَيۡتَةُ وَٱلدَّمُ وَلَحۡمُ ٱلۡخِنزِيرِ وَمَآ أُهِلَّ لِغَيۡرِ ٱللَّهِ بِهِۦ وَٱلۡمُنۡخَنِقَةُ
وَٱلۡمَوۡقُوذَةُ وَٱلۡمُتَرَدِّيَةُ وَٱلنَّطِيحَةُ وَمَآ أَكَلَ ٱلسَّبُعُ إِلَّا مَا ذَكَّيۡتُمۡ وَمَا ذُبِحَ عَلَى ٱلنُّصُبِ
وَأَن تَسۡتَقۡسِمُواْ بِٱلۡأَزۡلَٰمِۚ ذَٰلِكُمۡ فِسۡقٌۗ ٱلۡيَوۡمَ يَئِسَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن دِينِكُمۡ
فَلَا تَخۡشَوۡهُمۡ وَٱخۡشَوۡنِۚ ٱلۡيَوۡمَ أَكۡمَلۡتُ لَكُمۡ دِينَكُمۡ وَأَتۡمَمۡتُ عَلَيۡكُمۡ نِعۡمَتِي وَرَضِيتُ
لَكُمُ ٱلۡإِسۡلَٰمَ دِينٗاۚ فَمَنِ ٱضۡطُرَّ فِي مَخۡمَصَةٍ غَيۡرَ مُتَجَانِفٖ لِّإِثۡمٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٣﴾

**3.** (አማኞች ሆይ)፣ በክት፣ በሐይል ፈሳሽ ደም፣ የአሳማ ስጋ፣ ሲታረድ ከአላህ ስም ሌላ የተወሳበትም እንሰሳ፣ ታንቃ የሞተችም፣ ተደብድባ የተገደለች፣ በራሷ ተንከባላ የሞተችም፣ በቀንድ ተወግታ የሞተችና አውሬ የበላትም ከእነዚህ በሕይወት ላይ እያሉ ደርሳችሁ ያረዳችሁት ብቻ ሲቀር ለጣዖታትም የታረደና በአዝላም ድልን መፈለጋችሁ በእናንተ ላይ እርም ተደረገ። እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩትን መፈፀም በአላህ ላይ አመፅ ነው። ዛሬ እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ ከሀይማኖታችሁ ተስፋ ቆረጡ። ስለዚህ አትፍሩዋቸው። ይልቁን እኔን ብቻ ፍሩኝ። ዛሬ የሃይማኖታችሁን መመሪያ ሞላሁላችሁ። ፀጋየንም በእናንተ ላይ ፈፀምኩ። ለእናንተም በሃይማኖትነት ኢስላምን ወደድኩላችሁ*። በርሀብ ወቅት ወደ ኃጢአት ያዘነበለ ሳይሆን እርም የሆኑትን ነገሮች ለመብላት የተገደደ ሰው ሁሉ ለሕይወቱ ማቆያ ያህል ቢበላ ምንም ችግር የለበትም። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

* ይህ አንቀፅ የወረደው ጁሙዐ ቀን በዐረፋ ዕለት ከዐስር በኋላ ነቢዩ (ﷺ) በግመላቸው ላይ ሁነው ነው። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ኢብኑ ከሲር፤ ቁርጡቢና ኢብኑል ጀውዚ)

يَسۡـَٔلُونَكَ مَاذَآ أُحِلَّ لَهُمۡۖ قُلۡ أُحِلَّ لَكُمُ ٱلطَّيِّبَٰتُ وَمَا عَلَّمۡتُم مِّنَ ٱلۡجَوَارِحِ مُكَلِّبِينَ
تُعَلِّمُونَهُنَّ مِمَّا عَلَّمَكُمُ ٱللَّهُۖ فَكُلُواْ مِمَّآ أَمۡسَكۡنَ عَلَيۡكُمۡ وَٱذۡكُرُواْ ٱسۡمَ ٱللَّهِ عَلَيۡهِۖ وَٱتَّقُواْ
ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَرِيعُ ٱلۡحِسَابِ ٤ ٱلۡيَوۡمَ أُحِلَّ لَكُمُ ٱلطَّيِّبَٰتُۖ وَطَعَامُ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ
حِلّٞ لَّكُمۡ وَطَعَامُكُمۡ حِلّٞ لَّهُمۡۖ وَٱلۡمُحۡصَنَٰتُ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ وَٱلۡمُحۡصَنَٰتُ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ
ٱلۡكِتَٰبَ مِن قَبۡلِكُمۡ إِذَآ ءَاتَيۡتُمُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ مُحۡصِنِينَ غَيۡرَ مُسَٰفِحِينَ وَلَا مُتَّخِذِيٓ
أَخۡدَانٖۗ وَمَن يَكۡفُرۡ بِٱلۡإِيمَٰنِ فَقَدۡ حَبِطَ عَمَلُهُۥ وَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٥

**4-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሙስሊሞች) ለመብላት ምን ምን እንደተፈቀደላቸው ይጠይቁሃል። እናም ለእናንተ መልካሞች ሁሉ እና እነዚያም አላህ ካሳወቃችሁ አሰልጣኞች ሆናችሁ ያስተማራችኋቸው አዳኞች ያደኑት ሁሉ ተፈቀደላችሁ በላቸው። አላህ ካስተማራችሁ እውቀት ታስተምሯቸዋላችሁ። ከያዙላችሁ ነገር ላይ ብሉ። የአላህንም ስምም አውሱ። አላህን ፍሩ። አላህ ምርመራው ፈጣን ነውና። (አማኞች ሆይ)፤ ዛሬ መልካም ነገሮች ለእናንተ ተፈቀዱ። የእነዚያ መጽሐፍን የተሰጡ ሰዎች ምግብም ለእናንተ የተፈቀደ ነው። ምግባችሁም ለእነርሱ የተፈቀደ ነው። ከምዕመናት ሴቶችም ጥብቆቹ፤ ከእነዚያ ከናንተ በፊት መጽሐፍን ከተሰጡ ህዝቦች ሴቶችም መካከል ጥብቆቹና ዝሙተችና የሚስጥር ወዳጅ ያዢዎች ያልሆኑትን ጥብቆች ሆናችሁ መህሮቻቸውን በሰጣችኋቸው ጊዜ ልታገቡዋቸው የተፈቀዱ ናቸው። በአላህ ካመነ በኋላ ከእምነቱ ወደ ክህደት የሚመለስ ሰው በእርግጥ ስራው ተበላሸ። በመጨረሻም ቀን ከከሳሪዎች አንዱ ነው።

ከመዐዱ ምዕራፍ (4) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አባ ራፊዕ የተባለ ሰሃቢይ እንደዘገበው መልአኩ ጅብሪል ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ ወደ አሉበት ቦታ ለመግባት ሲያስፈቅድ እንዲገባ ቢፈቀድለትም አልገባም አለ። ለምንድ ነው የማትገባው? በማለት ነብዩ (ﷺ) ጠየቁት። እኛ እኮ ስዕልና ውሻ ያለበት ቤት አንገባም በማለት መለሰላቸው። በዚህ ጊዜ ነብዩ (ﷺ) ቤቶቹን ሲያስፈትሹ በአንድ ቤት ውስጥ የሞተ የውሻ ቡችላ በመገኘቱ ወዲያውኑ አባ ራዕፊ በመጥራት በመዲና ከተማ ውስጥ አንድም ውሻ ሳይቀር አጥፉ በማለት አዘዙት። አባ ራፊዕም ይህን ግዴታውን በመወጣ ላይ ሳለ ብቸኛ ነዋሪ የነበረችና ጠባቂዋ ውሻ የነበረች አንድት አሮጊት አግኝቶ ለማን እንደሚተዋት ተጨንቆ ባለበት ወቅት አንዳንድ ሰዎች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ምን አይነት ውሻ ነው ማሳደግ የሚፈቀድልን ብለው ሲጠይቁ መልስ ከመስጠት ተቆጥበው ባሉበት ወቅት ነው ይህ አንቀፅ የወረደና ለጥበቃና ለአደን ከሚሆኑ ውሾች በስተቀር መገደል ያለባቸው መሆኑን ያስረዳል። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከመዐዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ለእምነት ነክ ድንጋጌዎችና ለኢስላማዊ መግለጫዎች አክብሮት መስጠት እንደሚገባ፤
2. ለመልካም ተግባራትና ስራዎች ተፈፃሚነት በሙሉ ልብ ትብብር ማድረግ፤ በተቻለ አቅም እርዳታን መለገስ ግዴታ መሆኑንና በአንፃሩም ወንጀልን ለማሠራጨት ለሚደረግ እንቅስቃሴ ከተባባሪነት መታቀብ ግዴታ መሆኑን፤
3. ኢስላማዊ ስርአትን ባልተከተለና ሕገ ወጥ በሆነ መልኩ የታረዱና የበከቱ ከብቶችን ሥጋ ለጥንቆላና ለገድ መስዋዕት የሆኑ ከብቶችን ስጋ መመገብ የተከለከለ መሆኑን ነገር ግን በበሽታም ይሁን በተለያዩ ምክንያቶች ተዳክሞ የነበረን ከብት ሕይወቱ ሣያልፍ የደረሰ አርዶት ሊበላው የተፈቀደ መሆኑን፤
4. ለቀብሮችና ለአድባሮች የእርድ መስዋእት ማቅረብ የተከለከለ መሆኑን፤
5. መንፈሣዊ ፍርሃት የሚገባው ለአንድ አላህ ብቻ በመሆኑ እርሱን ብቻ መፍራት እንጂ ለካፊሮች ኃይል መርበትበት (መፍራት) የማይገባ መሆኑን፤
6. ኢስላም የተሟላ ድንጋጌ ያለው ሙሉ ኃይማኖት በመሆኑ አዳዲስ ነገሮችን በሃይማኖቱ ላይ በመጨመር የተሟላውን ሃይማኖት በፈጠራ (በቢድዐ) መበረዝ የተከለከለ መሆኑን፤
7. ነፍስን ለማዳንና የፀና ረሃብን ለማስታገስ በክትና ከአላህ ሌላ ከሆነ አካል መስዋእትነት የቀረበ እርዶችን ስጋ መብላት የተፈቀደ መሆኑን እንማራለን።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِذَا قُمْتُمْ إِلَى ٱلصَّلَوٰةِ فَٱغْسِلُوا۟ وُجُوهَكُمْ وَأَيْدِيَكُمْ إِلَى ٱلْمَرَافِقِ
وَٱمْسَحُوا۟ بِرُءُوسِكُمْ وَأَرْجُلَكُمْ إِلَى ٱلْكَعْبَيْنِ ۚ وَإِن كُنتُمْ جُنُبًا فَٱطَّهَّرُوا۟ ۚ وَإِن كُنتُم مَّرْضَىٰٓ
أَوْ عَلَىٰ سَفَرٍ أَوْ جَآءَ أَحَدٌ مِّنكُم مِّنَ ٱلْغَآئِطِ أَوْ لَـٰمَسْتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَلَمْ تَجِدُوا۟ مَآءً فَتَيَمَّمُوا۟
صَعِيدًا طَيِّبًا فَٱمْسَحُوا۟ بِوُجُوهِكُمْ وَأَيْدِيكُم مِّنْهُ ۚ مَا يُرِيدُ ٱللَّهُ لِيَجْعَلَ عَلَيْكُم مِّنْ حَرَجٍ
وَلَـٰكِن يُرِيدُ لِيُطَهِّرَكُمْ وَلِيُتِمَّ نِعْمَتَهُۥ عَلَيْكُمْ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ٦

**6.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ወደ ሶላት ለመግባት ባሰባችሁ ጊዜ ፊቶቻችሁንና እጆቻችሁን፤ እስከ ክርኖቻችሁ ድረስ እጠቡ። ራሶቻችሁን በውሃ አብሱ። እግሮቻችሁን እስከ ቁርጭምጭሚቶች* እጠቡ። ጀናባ ከሆናችሁ ሙሉ ገላችሁን ታጠቡ። በሽተኞች ወይም በጉዞ ላይ ብትሆኑ ወይም ከናንተ አንዳችሁ ከዓይነ ምድር ቢወጣ ወይም ሴቶችን ብትገናኙና ውሃን ባታገኙ በንፁህ የምድር አፈር ተይሙም አድርጉና። ከዚያ ለእሱ ፊታችሁንና እጆቻችሁን አብሱ። አላህ በእናንተ ላይ ምንም ችግር ሊያደርግ አይሻምና። ይልቁንም አላህን ታመሰግኑት ዘንድ ሊያጠራችሁና ፀጋውን በእናንተ ላይ ሊሞላ ይፈልጋል።

* ይህ ጉዳይ ሰፋ ያለ ክርክር ያለበት ነውና ሰፋፊ መፅሐፍቶችን መመልከት ያስፈልጋል። ከክርኖቻችሁ (ቁርጭምጭሚቶቻችሁ) ጋር ተብሎም ተተርጉሟል። ይህም ማለት በውዱእ ጊዜ ክርኖችን ቁርጭምጭሚቶችን ማጠብ ግዴታ ነው ማለት ነው።

ከመዐዱ ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- እሜቴ አይሻ እንዳሉት ከነብዩ (ﷺ) ጋር ከአንድ ዘመቻ ወደ መዲና በመግባት ላይ ሳሉ አንድ ቦታ ላይ እረፍት አድርገን ሳለን ነብዩ (ﷺ) በእኔ ላይ ተደግፈውና አረፍ እንዳሉ አባቴ አቡበክር ወደ እኔ በመምጣት ልጄ ሆይ! ሁል ጊዜ በአንቺ የተነሳ ሰዎች ይታገቱ? ለአንቺ ጌጣ ጌጥ ሲባል ያለውሃ ይታገቱ? እያለ ወቀሰኝ። በዚህ ጊዜ ነብዩ (ﷺ) ከእንቅልፋቸው ተነሱ። የሱብህ ሶላትም ደርሶ ነበር ውሃ ግን አልነበረም። በዚህ ውጥረት ላይ እያለን ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። ከዚያማ በኋላ እያንዳንዱ ሙስሊም እየተነሳ ዘራችሁ የበረካ ነው። በእናንተ የተነሳ ስንት ጉዳይ መፍትሄ አገኘ እያለ ያመሰግነን ጀመር። ይህ አንቀፅም የተየሙም አንቀፅ እየተባለ ይጠራል። (ቡኻሪ እና ሱዩጢ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ። «በትንሳኤ ቀን የኔ ሕዝቦች በውዱእ ምልክታቸው የተነሳ በብርሃን አሸብርቀው ይጠራሉ። ከእናንተ መካከል ብርሀኑ እንዲረዝምለት የፈለገ ሰው ይህን ይፈፅም ውዱእ በአግባቡ ይፈፅም» በዚህ ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) በቁርኣን ላይ እንዲታጠቡ ከገለፃቸው የውዱዕ አካላት ውጭ ተጨማሪ ቦታዎችን ውዱእ አድርገውባቸው አያውቁም።

وَٱذۡكُرُواْ نِعۡمَةَ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡ وَمِيثَٰقَهُ ٱلَّذِي وَاثَقَكُم بِهِۦٓ إِذۡ قُلۡتُمۡ سَمِعۡنَا وَأَطَعۡنَاۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٧ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُواْ قَوَّٰمِينَ لِلَّهِ شُهَدَآءَ بِٱلۡقِسۡطِۖ وَلَا يَجۡرِمَنَّكُمۡ شَنَـَٔانُ قَوۡمٍ عَلَىٰٓ أَلَّا تَعۡدِلُواْۚ ٱعۡدِلُواْ هُوَ أَقۡرَبُ لِلتَّقۡوَىٰۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ٨ وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٌ عَظِيمٞ ٩ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَآ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَحِيمِ ١٠

**7-10.** በእናንተ ላይ የለገሰውን የአላህ ፀጋና ያንንም ሰምተናል ታዘናልም ባላችሁ ጊዜ ያጠበቀባችሁን ቃል ኪዳኑን አስታውሱ። አላህን ፍሩ። አላህ በደረቶች ውስጥ ያለውን ሁሉ እንኳን ሳይቀር አዋቂ ነውና። እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ለአላህ የቆማችሁ ቀጥተኞች በትክክል መስካሪዎች ሁኑ። ሕዝቦችንም መጥላታችሁ ላለማስተካከል አይገፋፋችሁ ፍትሀዊ ሁኑ። ማስተካከል ለአላህ ፍራቻ በጣም የቀረበ ነው። አላህን ፍሩ። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና። እነዚያ በአላህ ያመኑና በጎ ስራዎችን የሰሩ ሰዎች ሁሉ አላህ ገነትን ቃል ገባላቸው። ለእነርሱ ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው። እነዚያም በአላህ የካዱና በአንቀፆቻችን ያስተባበሉ ሰዎች ሁሉ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡ إِذۡ هَمَّ قَوۡمٌ أَن يَبۡسُطُوٓاْ إِلَيۡكُمۡ أَيۡدِيَهُمۡ فَكَفَّ أَيۡدِيَهُمۡ عَنكُمۡۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلۡيَتَوَكَّلِ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١١

**11. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ሕዝቦች እጆቻቸውን ለጥቃት ወደ እናንተ ሊዘረጉ ባሰቡና እጆቻቸውን ከናንተ ላይ በከለከላቸው ጊዜ ለእናንተ የዋለላችሁን ፀጋ አስታውሱ። አላህን በትክክል ፍሩ። ትክክለኛ ምዕመናን ሁሉ በአላህ ላይ ብቻ ይመኩ።**

ከመዕዱ ምዕራፍ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- (ሀ) አንድ ቀን ነብዩ (ﷺ) አንድ ዛፍ ስር አረፍ ብለው ባሉበት አንድ ከሃዲ ዘላን በድንገት መጥቶ ሰይፋቸውን ካንጠለጠሉበት አንስቶ አሁን ከእኔ ማን ያድንሃል ሲላቸው ሶስት ጊዜ ሙሉ አላህ እያሉ ሰይፉ አምልጦት ወደቀ። ነብዩም (ﷺ) ሰይፉን ይዘው አንተንስ ከእኔ ማን ነው የሚያድነህ በማለት ሲጠይቁት የግል ችሮታህ ካልሆነ በስተቀር ማንም አለ። ነብዩም (ﷺ) ምንም ሳይሉት ሱሃቦችን ጠርተው ሁኔታውን ነገሯቸው በዚህ ጊዜ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ፤ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)

(ለ) የኡረይናህ እና የኡክል ሰዎች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው የመዲና ሁኔታ እንዳልተመቻቸው ህመም እንደፀናባቸው አየሩን እንደጠሉት አቤቱታ አቀረቡ። ከዚያም ነብዩ (ﷺ) ግመሎች ይኖሩበት ወደ ነበረበት ስፍራ እንዲሄዱና እዚያ ሲደርሱ የግመሎችንን ወተትና ሽንታቸውን እንዲጠጡ ይህም መድሃኒት እንደሚሆናቸው ነገሯቸው። ሰዎችም የተባለው ስፍራ ደርሰው የተባሉትን ሲያደርጉ ከበሽታቸው ዳኑና አገገሙ። ከዚያም የግመሉን እረኛ አሰቃቂ ግድያ ገድለው ግመሎቹን ዘርፈው አመለጡ። ነብዩ (ﷺ) እነኚህ ሰዎች የሰሩትን ወንጀል ሲሰሙ ሰራዊት ልከው ተይዘው እንዲመጡ አደረጉና ወንጀለኞቹ እረኛውን በገደሉበት አይነት ማለትም እግራቸውን እጃቸውን እንዲቆረጥ አይኖቻቸውም እንዲወጡ ትዕዛዝ ሰጡ። ተገድለው ሲያበቃ አስከሬናቸው በሜዳ ላይ እንዲጣል አደረገ። በዚህ ወቅትም ይህ አንቀፅ ወረደ። (ሙስሊም፤ ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከመዕዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (6-11) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የንፅህና የውዱእ የትጥበትና የተየሙም ሥነ ሥርዓትና አፈፃፀም እንዴት እንደሆነ፤
2. ለተየሙም የሚያበቁ ሸሪአዊ ምክንያቶች ዝርዝር ምን ምን እንደሆኑ፤
3. ውዱ እና ትጥበትን ግዴታ የሚያደርጉ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ፤
4. ዘወትር ለአላህ ፍፁም ታዛዥ ሆኖ መኖር ኢስላማዊ ግዴታ መሆኑን፤
5. ለምስክርነት ሲቀርቡ ትክክለኛውን እውነት ማስቀመጥ። በፍትህ አሰጣጥ ወቅትም ፍትሃዊነት ግዴታ መሆኑን በመገንዘብ በየትኛውም ቦታ ለማንኛውም የቅርብ ዘመድም ይሁን የሩቅ ሰው ፍትሃዊነት ግዴታ መሆኑን፤
6. የአላህን ማስጠንቀቂያ አዘል ዛቻና የመልካም ሥራ ቃሉን ሁልጊዜ ማስታወስ ተፈላጊ እንደሆነ፤
7. ሶላት መስገድ፤ ዘካን ለአላህ ሲሉ ገንዘብን መስጠት በነብዩ (ﷺ) ኡመት ላይ ብቻ ግዴታ የተደረጉ ኢስላማዊ ድንጋጌዎች ሣይሆን ከዚያ በፊት በነበሩት የቀደምት ነቢያት ሕዝቦች ላይ የተደነገጉ ግዴታዎች መሆናቸውን፤
8. ለነብዩ (ﷺ) አክብሮት መስጠት ከጎናቸው ሆኖ በተቻለ መጠን እርሳቸውን መርዳት ከኢስላማዊ ግዴታዎች አንዱ እንደሆነ እንማራለን።

۞ وَلَقَدۡ أَخَذَ ٱللَّهُ مِيثَٰقَ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ وَبَعَثۡنَا مِنۡهُمُ ٱثۡنَيۡ عَشَرَ نَقِيبٗاۖ وَقَالَ ٱللَّهُ إِنِّي مَعَكُمۡۖ
لَئِنۡ أَقَمۡتُمُ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَيۡتُمُ ٱلزَّكَوٰةَ وَءَامَنتُم بِرُسُلِي وَعَزَّرۡتُمُوهُمۡ وَأَقۡرَضۡتُمُ ٱللَّهَ قَرۡضًا
حَسَنٗا لَّأُكَفِّرَنَّ عَنكُمۡ سَيِّـَٔاتِكُمۡ وَلَأُدۡخِلَنَّكُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۚ فَمَن
كَفَرَ بَعۡدَ ذَٰلِكَ مِنكُمۡ فَقَدۡ ضَلَّ سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ١٢ فَبِمَا نَقۡضِهِم مِّيثَٰقَهُمۡ لَعَنَّٰهُمۡ وَجَعَلۡنَا
قُلُوبَهُمۡ قَٰسِيَةٗۖ يُحَرِّفُونَ ٱلۡكَلِمَ عَن مَّوَاضِعِهِۦ وَنَسُواْ حَظّٗا مِّمَّا ذُكِّرُواْ بِهِۦۚ وَلَا تَزَالُ تَطَّلِعُ
عَلَىٰ خَآئِنَةٖ مِّنۡهُمۡ إِلَّا قَلِيلٗا مِّنۡهُمۡۖ فَٱعۡفُ عَنۡهُمۡ وَٱصۡفَحۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٣

**12-13.** አላህ የኢስራኤል ልጆችን የጠበቀ ቃል ኪዳን ያዘባቸው። ከእነርሱም መካከል አስራ ሁለት አለቆች አስነሳን። አላህም አላቸው፡- እኔ ከናንተ ጋር ነኝ ሶላትን ደንቡን ጠብቃችሁ ብትሰግዱ፤ ግዴታ መጽዋትንም በትክክል ብትሰጡ በመልክተኞቼም በሙሉ ብታምኑና በሚያደርጉት ትግል ብትረዷቸው፡ ለአላህ መልካም ብድርን ብታበድሩ ኃጢአቶቻችሁን አብስላችኋለሁ። ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶችም በእርግጥ አስገባችኋለሁ። ከዚህም በኋላ ከናንተ መካከል በአላህ የካደ ሰው ግን ከቀጥተኛው መንገድ ተሳሳተ። ቃል ኪዳናቸውን በማፍረሳቸው ረገምናቸው። ልቦቻቸውንም ደረቆች አደረግን። ቃላትን ከቦታዎቻቸው ይለውጣሉ። ከታዘዙትም ነገር ከፊሉን ተው። ከእነርሱም ጥቂቶቹ ሲቀሩ ክዳትን ከማየት አትወገድም። ለእነርሱ ይቅርታ አድርግ። እለፋቸውም። አላህ መልካም ሰሪዎችን ሁሉ ይወዳልና።

وَمِنَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّا نَصَٰرَىٰٓ أَخَذۡنَا مِيثَٰقَهُمۡ فَنَسُواْ حَظّٗا مِّمَّا ذُكِّرُواْ بِهِۦ فَأَغۡرَيۡنَا بَيۡنَهُمُ
ٱلۡعَدَاوَةَ وَٱلۡبَغۡضَآءَ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِۚ وَسَوۡفَ يُنَبِّئُهُمُ ٱللَّهُ بِمَا كَانُواْ يَصۡنَعُونَ ١٤

**14.** ከእነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት ክፍሎች የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን። ሆኖም ከታዘዙበት ነገር ከፊሉን ተው። ስለዚህ እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ በመካከላቸው ጠብንና ጥላቻን ጣልንባቸው። አላህም ይሰሩት የነበሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል።

يَٰٓأَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ قَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولُنَا يُبَيِّنُ لَكُمۡ كَثِيرٗا مِّمَّا كُنتُمۡ تُخۡفُونَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَيَعۡفُواْ
عَن كَثِيرٖۚ قَدۡ جَآءَكُم مِّنَ ٱللَّهِ نُورٞ وَكِتَٰبٞ مُّبِينٞ ١٥ يَهۡدِي بِهِ ٱللَّهُ مَنِ ٱتَّبَعَ رِضۡوَٰنَهُۥ سُبُلَ
ٱلسَّلَٰمِ وَيُخۡرِجُهُم مِّنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ بِإِذۡنِهِۦ وَيَهۡدِيهِمۡ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ١٦

**15-16.** እናንተ የመጽሐፍ ባለቤቶች ሆይ! ከመጽሐፍ መካከል ትሸሽጉት ከነበራችሁት ነገር ብዙውን ለእናንተ የሚገልፅ ብዙውንም (ይቅር) የሚተው ሲሆን መልዕክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላችሁ። ከአላህ ዘንድም ብርሃንና ገላጭ የሆነ መፅሐፍ በእርግጥ መጣላችሁ። አላህ ውዴታውን የተከተሉ ሰዎች ሁሉ የሰላምን መንገዶች በእርሱ ይመራቸዋል። በፈቃዱም ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣቸዋል። ወደ ቀጥተኛም መንገድ ይመራቸዋል።

ከመዐዱ ምዕራፍ ከ (15-16) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አይሁድ ወደ ነብዩ (ﷺ) ይመጡና ዝሙተኛን ቀጥቅጦ ስለመግደል ሲጠይቃቸው። ከመሃላችሁ አዋቂ ማን ነው በማለት ሲጠየቋቸው ሰዎችም አብደላህ ቢን ሱርያን በማመላከት እሱ ነው አሏቸው። ነብዩ (ﷺ) ወደ እሱ ዞር በማለት ተውራትን በሙሳ ላይ ባወረደ፤ የጡር ጋራን በተከለ ጌታ ይሁንብኝ እውነቱን ንገረኝ በማለት ሲጠይቁት ሰውነቱ መንቀጥቀጥ ጀመረ እና ትንሽ እንደመረጋጋት ካለ በኋላ በእኛ ውስጠት ዝሙት ሲበዛ ጊዜ መቶ ጅራፍ ገረፈን። ራስን መላጨት ጀመርን በማለት ውስጣዊ እምነት አዘል የሆነ አባባል ሲናገር ነብዩ (ﷺ) ቀጥቅጠው እንዲገድሉት በመወሰን አሰናበቷቸው። በዚህ ጊዜ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ዋሒዲ)

لَّقَدۡ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ مَرۡيَمَۚ قُلۡ فَمَن يَمۡلِكُ مِنَ ٱللَّهِ شَيۡـًٔا إِنۡ
أَرَادَ أَن يُهۡلِكَ ٱلۡمَسِيحَ ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَأُمَّهُۥ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗاۗ وَلِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَاۚ يَخۡلُقُ مَا يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ١٧

**17.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ አላህ ማለት የመርየም ልጅ አልመሲህ ነው ያሉ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ በአላህ ካዱ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የመርየምን ልጅ አልመሲህንና እናቱን እንደዚሁም በምድር ያለንም ፍጡር ሁሉ ለማጥፋት ቢሻ ከአላህ ማዳን የሚችል ማን ነው? የሰማያትና የምድር የመካከላቸውም ንግስና የአላህ ብቻ ነው። የሚፈልገውን ይፈጥራል። አላህ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነውና በላቸው።

وَقَالَتِ ٱلۡيَهُودُ وَٱلنَّصَٰرَىٰ نَحۡنُ أَبۡنَٰٓؤُاْ ٱللَّهِ وَأَحِبَّٰٓؤُهُۥۚ قُلۡ فَلِمَ يُعَذِّبُكُم بِذُنُوبِكُمۖ بَلۡ
أَنتُم بَشَرٞ مِّمَّنۡ خَلَقَۚ يَغۡفِرُ لِمَن يَشَآءُ وَيُعَذِّبُ مَن يَشَآءُۚ وَلِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ
وَمَا بَيۡنَهُمَاۖ وَإِلَيۡهِ ٱلۡمَصِيرُ ١٨

**18.** አይሁዶችና ክርስቲያኖች እኛ የአላህ ልጆችና ወዳጆች ነን አሉ። ታዲያ በኃጢአቶቻችሁ ለምን ይቀጣችኋል? አይደላችሁም። እናንተ ከፈጠራቸው ሰዎች መካከል ውስን ክፍሎች ናችሁ። አላህ ለሚሻው ሰው ይምራል።

የሚሻውን ሰው ይቀጣል። የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ንግስናው የአላህ ብቻ ነው። የሁሉም መመለሻው ወደ እርሱ ብቻ ነው በላቸው።

ከመዐዱ ምዕራፍ (18) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁዶችና ነሷሮች ወደ ነብዩ በመምጣት እያነጋገሯቸው ሳለ ነብዩ ወደ አላህ ጠርቸዋለሁ። እንቢ ካሉ ሊደርስባቸው የሚችለው ቅጣት ሲያስጠነቅቋቸው ሙሐመድ ምን ታስፈራራኛለህ እኛ የአላህ ወንድ ልጆችና ወዳጆቹ ነን እኮ በማለታቸው ነው የወረደው።

يَـٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَـٰبِ قَدْ جَآءَكُمْ رَسُولُنَا يُبَيِّنُ لَكُمْ عَلَىٰ فَتْرَةٍ مِّنَ ٱلرُّسُلِ أَن تَقُولُوا۟ مَا جَآءَنَا
مِنۢ بَشِيرٍ وَلَا نَذِيرٍ ۖ فَقَدْ جَآءَكُم بَشِيرٌ وَنَذِيرٌ ۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ١٩

**19.** እናንተ የመጽሐፍ ሰዎች ሆይ፣ አብሳሪና አስፈራሪ አልመጣልንም እንዳትሉ ከመልዕክተኞቻችን በተቋረጡበት ጊዜ (መመሪያችን) የሚያብራራ ሆኖ መልዕክተኛችን (ሙሐመድ) በእርግጥ መጣላቸው። አብሳሪና አስፈራሪም በእርግጥ መጣላችሁ። አላህም በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነውና።

وَإِذْ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوْمِهِۦ يَـٰقَوْمِ ٱذْكُرُوا۟ نِعْمَةَ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ إِذْ جَعَلَ فِيكُمْ أَنۢبِيَآءَ
وَجَعَلَكُم مُّلُوكًا وَءَاتَىٰكُم مَّا لَمْ يُؤْتِ أَحَدًا مِّنَ ٱلْعَـٰلَمِينَ ٢٠ يَـٰقَوْمِ ٱدْخُلُوا۟ ٱلْأَرْضَ
ٱلْمُقَدَّسَةَ ٱلَّتِى كَتَبَ ٱللَّهُ لَكُمْ وَلَا تَرْتَدُّوا۟ عَلَىٰٓ أَدْبَارِكُمْ فَتَنقَلِبُوا۟ خَـٰسِرِينَ ٢١

**20-21.** ሙሳ ለሕዝቦቹ፡- ሕዝቦቼ ሆይ፣ የአላህን ጸጋ በውስጣችሁ ነብያትን ባደረገ፤ ነገስታትንም ባደረጋችሁና ከአለማት ህዝብ ለአንድም ያልሰጠውን ችሮታ በሰጣችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ የዋለውን ፀጋ አስታውሱ። «ሕዝቦቼ ሆይ! ያችን አላህ ለእናንተ ያደረጋትን የተቀደሰችውን መሬት ግቡ። ወደ ኋላችሁም አትመለሱ። ከሳሪዎች ሆናችሁ ትመለሳላችሁና።»

قَالُوا۟ يَـٰمُوسَىٰٓ إِنَّ فِيهَا قَوْمًا جَبَّارِينَ وَإِنَّا لَن نَّدْخُلَهَا حَتَّىٰ يَخْرُجُوا۟ مِنْهَا فَإِن يَخْرُجُوا۟ مِنْهَا
فَإِنَّا دَٰخِلُونَ ٢٢ قَالَ رَجُلَانِ مِنَ ٱلَّذِينَ يَخَافُونَ أَنْعَمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِمَا ٱدْخُلُوا۟ عَلَيْهِمُ ٱلْبَابَ
فَإِذَا دَخَلْتُمُوهُ فَإِنَّكُمْ غَـٰلِبُونَ ۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَتَوَكَّلُوٓا۟ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ٢٣ قَالُوا۟ يَـٰمُوسَىٰٓ إِنَّا
لَن نَّدْخُلَهَآ أَبَدًا مَّا دَامُوا۟ فِيهَا ۖ فَٱذْهَبْ أَنتَ وَرَبُّكَ فَقَـٰتِلَآ إِنَّا هَـٰهُنَا قَـٰعِدُونَ ٢٤

**22-24.** ሙሳ ሆይ፣ በእርሷ ውስጥ ሀያላን ህዝቦች ስላሉ ከእርሷ እስከሚወጡ ድረስ ፈፅሞ አንገባም። ከወጡ ግን ገቢዎች ነን አሉ። ከእነዚያ አላህን ከሚፈሩትና አላህ ፀጋውን ከለገሰላቸው ሰዎች መካከል ሁለት ሰዎች በእነርሱ በሀያሎቹ ላይ በሩን ግቡ። በገባችሁ ጊዜ እናንተ አሸናፊዎች ናችሁ። ትክክለኛ ምዕመናን እንደሆናችሁ በአላህ ላይ ብቻ ተመኩ አሏቸው። ሙሳ ሆይ!፣ እነርሱ በውስጧ እስካሉ ድረስ ፈፅሞ ምን ጊዜም አንገባም። ስለዚህ አንተና ጌታህ ሂዱና ተዋጉ። እኛ እዚህ ተቀማጮች ነን አሉ።

**ከመዐዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (12-23) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከየትኛውም ወገን ጋር የሚደረጉ የቃል ኪዳን ስምምነቶችን ማክበር ግዴታ መሆኑና በተለይ ደግሞ የአላህ ባሪያዎች ለአላህ የሚገቡ ቃሎችን በተለየ መልኩ ማክበርና ለተፈጻሚነታቸው በሙሉ አቅማቸው መንቀሳቀስ ግዴታቸው መሆኑን፤
2. አይሁድ ክህደትን ለመተግበር ወደ ኋላ የማይሉና ይህም መለያ ባህሪያቸው እንደሆነ፤
3. ነገሮችን እያከረሩ እስጥ እገባ ውስጥ ከመነከርና እልህ ከመያያዝ ይልቅ ቶሎ በትዕግስት ማሳለፍ ተወዳጅ እንደሆነ፤
4. ነሳራዎችም ይሄን መጥፎ ባህርያት የወረሱ፤ እምነት ሊጣልባቸው የማይገባ ሕዝቦች መሆናቸውን
5. አይሁድ ኢስላም ተቀብለው ትክክለኛውን እምነት እንዲይዙ አላህ የሰጣቸው ምክር አዘል ንግግር ይዘት ምን እንደሚመስል፤
6. አይሁድና ነሳራዎች ከአላህ የወረዱ አያሌ ሰማያዊ ሕግጋቶችንና ድንጋጌዎችን መካዳቸው፤
7. የነብዩን (ﷺ) ፈለግ (ሱና) መከተል ለሰው ልጅ ተድላና ምቾትን የሚያጎናፅፍ ዋነኛ የደስታ ምንጭ መሆኑን፤
8. ቁርአን ሰዎች ቀና መንገድ በመያዝ መልካሙን ሁሉ እንዲጨብጡ የሚያመለክተ መመሪያና የሕይወትን መስመር የማሳመር ዋስትና የሚሰጥ መሆኑን፤
9. አላህ ለእርሱ በማይገቡና የእሱ ባልሆኑ ባህርያት የገለፀ ሰው ወደ ኩፍር እንደሚገባ፤
10. አይሁድና ነሳራዎች እኛ የአላህ መንፈሳዊ ልጆችና ወዳጆች ነን ሲሉ የሚነዙት ወሬ የሐሰት ፕሮፖጋንዳቸው መሆኑን፤
11. ፍጡራን በሙሉ ከአላህ ጋር ያላቸው ግንኙነት የፍጡርና የፈጣሪ ግንኙነት ብቻ እንደሆነ፤
12. አላህ ነብዩን (ﷺ) ወደዚህች ምድር በመላከ የመፅሐፍ ባለቤቶች የሆኑት አይሁድና ነሳራዎች የሚያቀርቧቸው መሰረተ ቢስ ምክንያቶች በሙሉ ውድቅ ማድረጉንና ምክንያት እንዳያቀረቡ በር መዝጋቱን፤
13. ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በተንኮልና ሴራ ብስጭት እንዳይገባቸው አላህ ለነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) የላከውን የማፅናኛ ቃል ይዘት፤
14. በየትኛውም ዘመን አላህን የሚፈሩ ልባቸው በእምነት የተሞላ የአላህ ፍፁም አገልጋይ ባሪያዎች የማይጠፉ መሆኑን፤
15. በጦርነት ወቅት በድንገት ወረራ በማድረግ የጠላትን ጦር ማጥቃት ድልን ለመቀዳጀት ያለውን አስተዋፅኦ እንማራለን።

قَالَ رَبِّ إِنِّي لَآ أَمۡلِكُ إِلَّا نَفۡسِي وَأَخِيۖ فَٱفۡرُقۡ بَيۡنَنَا وَبَيۡنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡفَٰسِقِينَ ٢٥

25. (ሙሳም) ጌታዬ ሆይ፣ እኔ ራሴንና ወንድሜን እንጂ ማንንም ላስገድድ አልችልም። ስለዚህ በእኛና በአመፀኞቹ ሕዝቦች መካከል ለይ (ተገቢ ፍርድህን ስጥ አሉ)።

قَالَ فَإِنَّهَا مُحَرَّمَةٌ عَلَيۡهِمۡۛ أَرۡبَعِينَ سَنَةٗۛ يَتِيهُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ فَلَا تَأۡسَ عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡفَٰسِقِينَ ٢٦

26. አላህ ያቺ የተቀደሰችው መሬት በእነርሱ ላይ ለአርባ አመት ያህል እርም ናት። በምድረ በዳ ይንከራተታሉ። (እናም ሙሳ ሆይ)፣ በአመፀኞችም ሕዝቦች ላይ አትዘን አለው።

۞وَٱتۡلُ عَلَيۡهِمۡ نَبَأَ ٱبۡنَيۡ ءَادَمَ بِٱلۡحَقِّ إِذۡ قَرَّبَا قُرۡبَانٗا فَتُقُبِّلَ مِنۡ أَحَدِهِمَا وَلَمۡ يُتَقَبَّلۡ مِنَ
ٱلۡأٓخَرِ قَالَ لَأَقۡتُلَنَّكَۖ قَالَ إِنَّمَا يَتَقَبَّلُ ٱللَّهُ مِنَ ٱلۡمُتَّقِينَ ٢٧ لَئِنۢ بَسَطتَ إِلَيَّ يَدَكَ لِتَقۡتُلَنِي
مَآ أَنَا۠ بِبَاسِطٖ يَدِيَ إِلَيۡكَ لِأَقۡتُلَكَۖ إِنِّيٓ أَخَافُ ٱللَّهَ رَبَّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢٨ إِنِّيٓ أُرِيدُ أَن تَبُوٓأَ
بِإِثۡمِي وَإِثۡمِكَ فَتَكُونَ مِنۡ أَصۡحَٰبِ ٱلنَّارِۚ وَذَٰلِكَ جَزَٰٓؤُاْ ٱلظَّٰلِمِينَ ٢٩ فَطَوَّعَتۡ لَهُۥ نَفۡسُهُۥ
قَتۡلَ أَخِيهِ فَقَتَلَهُۥ فَأَصۡبَحَ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٣٠ فَبَعَثَ ٱللَّهُ غُرَابٗا يَبۡحَثُ فِي ٱلۡأَرۡضِ
لِيُرِيَهُۥ كَيۡفَ يُوَٰرِي سَوۡءَةَ أَخِيهِۚ قَالَ يَٰوَيۡلَتَىٰٓ أَعَجَزۡتُ أَنۡ أَكُونَ مِثۡلَ هَٰذَا ٱلۡغُرَابِ
فَأُوَٰرِيَ سَوۡءَةَ أَخِيۖ فَأَصۡبَحَ مِنَ ٱلنَّٰدِمِينَ ٣١

27-31. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእነርሱ ላይ የአደምን ሁለት ልጆች ወሬ (ማለትም) ሁለቱም ቁርባን ባቀረቡና አላህ ከአንደኛቸው ተቀብሎ ከሌላው ባልተቀበለበት ጊዜ የሆነውን ታሪክ አንብብላቸው። ተቀባይነት ያጣው ልጃቸው ወንድሙን እገድልሃለሁ* አለው። ተገዳዩ ግን አላህ የሚቀበለው እኮ ከጥንቁቆቹ ሰዎች ብቻ ነው አለ። ልትገድለኝ እጅህን ወደ እኔ ብትዘረጋ እንኳን እኔ ልገድልህ እጄን ወደ አንተ የምዘረጋ አይደለሁም። እኔ የአለማትን ጌታ አላህን እፈራለሁና አለ። እኔ በኃጢአቴና በኃጢአትህ ወደ ጌታህ ልትመለስና ከእሳት ጓዶች አንዱ ልትሆን እሻለሁ። ይህም የበደለኞች ቅጣት ነው (አለ)። ነፍሱም ወንድሙን መግደል ሸለመችለትና ገደለው። ከከሳሪዎችም ሆነ። የወንድሙን እሬሳ እንዴት እንደሚቀብር ያሳየው ዘንድ አላህ መሬትን የሚጭር ቁራ ላከለት። ወይኔ የወንድሜን እሬሳ እቀብር ዘንድ እንደዚህ ቁራ መሆን እንኳን አቃተኝን? አለ። ከዚያ ከፀፀተኞች ሆነ።

✴ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «የአደም የመጀመሪያው ልጅ የሰው መገደልን ባሕል ፈጥሮ በኃላፊነት ተጠያቂ እስከሆነበት ድረስ ማንኛውም ነፍስ አትገደልም ነበር።»

مِنۡ أَجۡلِ ذَٰلِكَ كَتَبۡنَا عَلَىٰ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ أَنَّهُۥ مَن قَتَلَ نَفۡسَۢا بِغَيۡرِ نَفۡسٍ أَوۡ فَسَادٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَكَأَنَّمَا قَتَلَ ٱلنَّاسَ جَمِيعٗا وَمَنۡ أَحۡيَاهَا فَكَأَنَّمَآ أَحۡيَا ٱلنَّاسَ جَمِيعٗاۚ وَلَقَدۡ جَآءَتۡهُمۡ رُسُلُنَا بِٱلۡبَيِّنَٰتِ ثُمَّ إِنَّ كَثِيرٗا مِّنۡهُم بَعۡدَ ذَٰلِكَ فِي ٱلۡأَرۡضِ لَمُسۡرِفُونَ ٣٢

32. በዚህ ምክንያት በኢስራኢል ልጆች ላይ አንዲትን ንፁህ ነፍስን (ያልገደለችን) ወይም አንዲትን ነፍስ በምድር ላይ ያላጠፋችን ነፍስ የገደለ ሰው ሁሉ ሰዎችን ሁሉ እንደገደለ ሰው ነው። ህያው ያደረጋትም ሰው ሰዎችን ሁሉ ህያው እንዳደረገ ነው ማለትን ደነገግን መልዕክተኞቻችንም ግልፅን ተዐምራት አምጥተውላቸዋል። ከዚህም በኋላ ከእነርሱ ብዙዎቹ በምድር ላይ ወሰንን አላፊዎች ናቸው።

إِنَّمَا جَزَٰٓؤُاْ ٱلَّذِينَ يُحَارِبُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَيَسۡعَوۡنَ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَسَادًا أَن يُقَتَّلُوٓاْ أَوۡ يُصَلَّبُوٓاْ أَوۡ تُقَطَّعَ أَيۡدِيهِمۡ وَأَرۡجُلُهُم مِّنۡ خِلَٰفٍ أَوۡ يُنفَوۡاْ مِنَ ٱلۡأَرۡضِۚ ذَٰلِكَ لَهُمۡ خِزۡيٞ فِي ٱلدُّنۡيَاۖ وَلَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ عَذَابٌ عَظِيمٌ ٣٣ إِلَّا ٱلَّذِينَ تَابُواْ مِن قَبۡلِ أَن تَقۡدِرُواْ عَلَيۡهِمۡۖ فَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٣٤

33-34. የእነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚዋጉ፤ በምድር ላይ ለጥፋት የሚንቀሳቀሱ ሰዎች ሁሉ ቅጣት መገደል ወይም መሰቀል ወይም እጆቻቸውንና እግሮቻቸውን በማፈራረቅ መቆረጥ ወይም ከሀገር መባረር ነው። ይህ ቅጣት ለእነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ውርደት ነው። በመጨረሻይቱም ዓለም ከዚህ ሌላ ከባድ ቅጣት አለባቸው። (ሙስሊሞች ሆይ!) (ይህ ተግባር የሚፈፀመው) እነዚያ በእነርሱ ላይ ከመቻላችሁ በፊት የተፀፀቱ ሰዎች ሲቀሩ ነው። እናም አላህ መሀሪና አዛኝ መሆኑን እወቁ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱبۡتَغُوٓاْ إِلَيۡهِ ٱلۡوَسِيلَةَ وَجَٰهِدُواْ فِي سَبِيلِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ٣٥

35. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፤ አላህን ፍሩ። ወደ እርሱም የሚያቀርባችሁን ነገር✴ ሁሉ (መልካምን ስራ በመስራት) ፈልጉ። ትድኑ ዘንድም በእርሱ መንገድ ላይ ብቻ ታገሉ።

✴ አላህን ብቻ በመገዛት ወደሱ መቃረብን ፈልጉ።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَوْ أَنَّ لَهُم مَّا فِي ٱلْأَرْضِ جَمِيعًا وَمِثْلَهُۥ مَعَهُۥ لِيَفْتَدُواْ بِهِۦ مِنْ عَذَابِ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ مَا تُقُبِّلَ مِنْهُمْۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٣٦﴾ يُرِيدُونَ أَن يَخْرُجُواْ مِنَ ٱلنَّارِ وَمَا هُم بِخَٰرِجِينَ مِنْهَاۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ مُّقِيمٌ ﴿٣٧﴾

**36-37.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ በምድር ላይ ያለ ነገርን ሁሉ እና ከርሱ ጋርም መሰሉ ተጨምሮበት ከትንሳኤ ቀን ቅጣት ነፃ ለመሆን እርሱን ቤዛ ቢሰጡት ተቀባይነት ባላገኙ ነበር። ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። ከእሳት ሊወጡ ይፈልጋሉ። እነርሱ ግን ሁልጊዜም ከእርሷ ወጪዎች አይደሉም። ለእነርሱ ዘውታሪ ቅጣት አለባቸው።

وَٱلسَّارِقُ وَٱلسَّارِقَةُ فَٱقْطَعُوٓاْ أَيْدِيَهُمَا جَزَآءًۢ بِمَا كَسَبَا نَكَٰلًا مِّنَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٣٨﴾

**38.** የወንድ ሌባንና የሴት ሌባን ለሰሩት ወንጀል ከአላህ የሆነ መቀጫ ሲሆን እጆቻቸውን ቁረጡ።* አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

✷ *ረሀብና ሌላም የሚያስገድደው ችግር ሳይኖርበት ዋጋ የሚያወጣን ገንዘብ ከተቀመጠበት የሰረቀ እንደሆነ ነው።*

فَمَن تَابَ مِنۢ بَعْدِ ظُلْمِهِۦ وَأَصْلَحَ فَإِنَّ ٱللَّهَ يَتُوبُ عَلَيْهِۗ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٣٩﴾ أَلَمْ تَعْلَمْ أَنَّ ٱللَّهَ لَهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ يُعَذِّبُ مَن يَشَآءُ وَيَغْفِرُ لِمَن يَشَآءُۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ﴿٤٠﴾

**39-40.** ከበደለ በኋላ የተፀፀተና ስራውን ያሳመረ ሰው ሁሉ አላህ ፀፀቱን ይቀበለዋል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የሰማያትና የምድር ንግስና የእሱ ብቻ መሆኑን አላወክምን? የሚሻውን ሰው ይቀጣል። ለሚሻው ሰውም ይምራል። አላህ በነገሩ ላይ ሁሉ ቻይ ነውና።

۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلرَّسُولُ لَا يَحْزُنكَ ٱلَّذِينَ يُسَٰرِعُونَ فِي ٱلْكُفْرِ مِنَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ ءَامَنَّا بِأَفْوَٰهِهِمْ وَلَمْ تُؤْمِن قُلُوبُهُمْۛ وَمِنَ ٱلَّذِينَ هَادُواْۛ سَمَّٰعُونَ لِلْكَذِبِ سَمَّٰعُونَ لِقَوْمٍ ءَاخَرِينَ لَمْ يَأْتُوكَۖ يُحَرِّفُونَ ٱلْكَلِمَ مِنۢ بَعْدِ مَوَاضِعِهِۦۖ يَقُولُونَ إِنْ أُوتِيتُمْ هَٰذَا فَخُذُوهُ وَإِن لَّمْ تُؤْتَوْهُ فَٱحْذَرُواْۚ وَمَن يُرِدِ ٱللَّهُ فِتْنَتَهُۥ فَلَن تَمْلِكَ لَهُۥ مِنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔاۚ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَمْ يُرِدِ ٱللَّهُ أَن يُطَهِّرَ

قُلُوبُهُمۡۚ لَهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَا خِزۡيٞۖ وَلَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ عَذَابٌ عَظِيمٞ ﴿٤١﴾ سَمَّٰعُونَ لِلۡكَذِبِ أَكَّٰلُونَ
لِلسُّحۡتِۚ فَإِن جَآءُوكَ فَٱحۡكُم بَيۡنَهُمۡ أَوۡ أَعۡرِضۡ عَنۡهُمۡۖ وَإِن تُعۡرِضۡ عَنۡهُمۡ فَلَن يَضُرُّوكَ
شَيۡـٔٗاۖ وَإِنۡ حَكَمۡتَ فَٱحۡكُم بَيۡنَهُم بِٱلۡقِسۡطِۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُقۡسِطِينَ ﴿٤٢﴾

**41-42.** መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! እነዚያ ወደ ክህደት የሚቻኮሉት ሰዎች ልቦቻቸው ሳያምኑ በአፎቻቸው ብቻ አመንን ያሉትና (መናፍቃንና) አይሁድ አያሳዝኑህ። እነርሱ ውሸትን ብቻ አድማጮች ናቸውና። ገና ወደ አንተ ላልመጡ ለሌሎች ሕዝቦች አድማጮች ናቸው። ንግግሮችን ከስፍሮቻቸው ወደ ሌላ በመቀየር መልዕክት ያጣምማሉ። ይህንን የተጣመመውን ብትሰጡት ያዙት። ካልተሰጣችሁትም ተጠንቀቁ ይላሉ። አላህ መፈተንን የሚሻበትን ሰው ሁሉ ለእርሱ ከአላህ ለመከላከል ፍፁም አትችልም። እነዚያ ማለት አላህ ልቦቻቸውን ማጥራትን ያልሻላቸው ሰዎች ናቸው። ለእነርሱም በቅርቢቱ ዓለም ውርደት አለባቸው። ለእነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለምም ሌላ ከባድ ቅጣት አለባቸው። እነርሱ ውሸትን አድማጮች፤ እርም የሆኑ ነገሮችን በላተኞች ናቸው። ለዳኝነት ወደ አንተ ዘንድ ከመጡ በመካከላቸው በትክክል ፍረድ። ወይም ተዋቸው። ብትተዋቸው ምንም አይጎዱሁም። ከፈረድክ ግን በመካከላቸው በትክክል ፍረድ። አላህ በትክክል ፈራጆችን ይወዳልና።

وَكَيۡفَ يُحَكِّمُونَكَ وَعِندَهُمُ ٱلتَّوۡرَىٰةُ فِيهَا حُكۡمُ ٱللَّهِ ثُمَّ يَتَوَلَّوۡنَ مِنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَۚ وَمَآ
أُوْلَٰٓئِكَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٤٣﴾ إِنَّآ أَنزَلۡنَا ٱلتَّوۡرَىٰةَ فِيهَا هُدٗى وَنُورٞۚ يَحۡكُمُ بِهَا ٱلنَّبِيُّونَ ٱلَّذِينَ
أَسۡلَمُواْ لِلَّذِينَ هَادُواْ وَٱلرَّبَّٰنِيُّونَ وَٱلۡأَحۡبَارُ بِمَا ٱسۡتُحۡفِظُواْ مِن كِتَٰبِ ٱللَّهِ وَكَانُواْ عَلَيۡهِ
شُهَدَآءَۚ فَلَا تَخۡشَوُاْ ٱلنَّاسَ وَٱخۡشَوۡنِ وَلَا تَشۡتَرُواْ بِـَٔايَٰتِي ثَمَنٗا قَلِيلٗاۚ وَمَن لَّمۡ يَحۡكُم بِمَآ
أَنزَلَ ٱللَّهُ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴿٤٤﴾ وَكَتَبۡنَا عَلَيۡهِمۡ فِيهَآ أَنَّ ٱلنَّفۡسَ بِٱلنَّفۡسِ وَٱلۡعَيۡنَ
بِٱلۡعَيۡنِ وَٱلۡأَنفَ بِٱلۡأَنفِ وَٱلۡأُذُنَ بِٱلۡأُذُنِ وَٱلسِّنَّ بِٱلسِّنِّ وَٱلۡجُرُوحَ قِصَاصٞۚ فَمَن تَصَدَّقَ
بِهِۦ فَهُوَ كَفَّارَةٞ لَّهُۥۚ وَمَن لَّمۡ يَحۡكُم بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٤٥﴾

**43-45.** እነርሱ ዘንድ በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለበት ተውራት ያለ ሲሆን እንዴት ያስፈርዱሃል። ከዚያስ በኋላ እንዴት ይሸሻሉ። እነዚያ በፍፁም ትክክለኛ አማኞች አይደሉም። ተውራትን በውስጡ ለሰዎች መመሪያና ብርሃን ያለባት ሲሆን አወረድነው። እነዚያ ትዕዛዙን የተቀበሉት ነብያት ሁሉ

በእርሱ ይፈርዳሉ። ሊቃውንትና አዋቂዎች ከአላህ መጽሐፍን እንዲጠብቁ በተደረጉትና በእርሱ ላይ መስካሪዎች በመሆናቸው እንዲሁ በሱ ይፈርዳሉ። እናም ሰዎችን አትፍሩ። እኔን ብቻ ፍሩኝ። በአንቀፆቼም አነስተኛን ዋጋ አትለውጡ (አትግዙ)። እነዚያ አላህ ባወረደው መመሪያ ያልፈረዱ ሰዎች ሁሉ ከሐዲያን ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። በእነርሱም ላይ በውስጡ ነፍስን በነፍስ፤ አይንን በአይን፤ አፍንጫን በአፍንጫ፤ ጆሮን በጆሮ፤ ጥርስን በጥርስ፤ ይያዛል። ቁስሎችንም ማመሳሰል ግዴታ አለባቸው ብለን ደነገግን። ይህንን መብቱን ሰው ሁሉ እርሱ ለሰራው ኃጢአት ማስረገዣ ነው። አላህ ባወረደው መመሪያ የማይፈርዱ ሰዎችን ሁሉ እነዚያ በደለኞቹ ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው።

وَقَفَّيْنَا عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِم بِعِيسَى ٱبْنِ مَرْيَمَ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ ٱلتَّوْرَىٰةِ ۖ وَءَاتَيْنَٰهُ ٱلْإِنجِيلَ فِيهِ هُدًى وَنُورٌ وَمُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ مِنَ ٱلتَّوْرَىٰةِ وَهُدًى وَمَوْعِظَةً لِّلْمُتَّقِينَ ﴿٤٦﴾ وَلْيَحْكُمْ أَهْلُ ٱلْإِنجِيلِ بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ فِيهِ ۚ وَمَن لَّمْ يَحْكُم بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْفَٰسِقُونَ ﴿٤٧﴾

**46-47.** በፈለጎቻቸውም (በነብያቶች ፈለግ) ላይ የመርየምን ልጅ ዒሳን✳ ከተውራት በስተፊት ያለውን አረጋጋጭ ሲሆን አስከተልን። ኢንጅልም በውስጡ ቀጥተኛ መመሪያና ብርሃን ያለበት በስተፊቱ ያለውን ተውራትን የሚያረጋግጥ ለጥንቁቆቹም መሪና ገሳጭ የሆነውን ሰጠነው። የኢንጂል ባለቤቶች በውስጡ አላህ ባወረደው ህግ ይፍረዱ። አላህ ባወረደው የማይፈርዱ ሰዎች ሁሉ አመፀኞች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው።

✳ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ እንዲህ ብለዋል፦ «ከሰዎች በበለጠ ለመርየም ልጅ በጣም የቀረብኩት ነኝ። ሁሉም ነብያት ወንድማማች ናቸው። በእኔና በእሱ መካከል ነብይ አልነበረም»

ከመዐዱ ከ (41-47) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ አይሁዶች አንድ ሰውዬ ከሰል ለቅልቀው እየገረፉ በመንገድ ሲሄዱ ነብዩ (ﷺ) ተመለከቱና ለምንድ ነው ይህን ሰው በዚህ አይነት የምትቀጡት ብለው አይሁድን ጠየቋቸው እነርሱም ሰውየው ዝሙት ስለ ሰራ መሆኑን ነገሯቸው። ነብዩም (ﷺ) በእናንተ መፅሐፍ የዝሙት ቅጣት በዚህ አይነት ሁኔታ እንዲሆን ተደንግጓልን? አሏቸው። አይሁዳውያኑ አዎን ሲሉ አረጋገጡላቸው ከዚያም ነብዩ (ﷺ) ከአይሁድ ምሁራን አንዱን አዋቂ ጠርተው ሲያበቁ በሙሳ ላይ ተውራትን ባወረደው በፈጣሪ አላህ እማፀንሃለሁ በእናንተ መፅሐፍ የዝሙት ቅጣት ድንጋጌ ይህን የመሰለ ቅጣትን ደንግጓልን? በማለት ጠየቁት። የአይሁድ አዋቂውም ሙሐመድ ሆይ! ከጌታህ በአላህ ስም ስለጠየከኝ እንጂ እውነቱ አልነግርህም ነበር በእርግጥ በተውራት ህግ መሰረት ዝሙት የሰራ ሰው የሚፈፀምበት ቅጣት ተቀጥቅጦ እንዲገደል የሚያዝ ድንጋጌ ነው። ሆኖም ትላለቅ ሰዎች በብዛት ዝሙት እየሰሩ በመገኘታቸውና ይህንን የተውራት ድንጋጌ ደግሞ በእነርሱ ላይ ተግባራዊ ማድረጉ በጣም ስለከበደን ሁሉም ሰው ተመሳሳይ ቅጣት ያገኝ ዘንድ ይህንን የቅጣት አይነት ራሳችን ደነገግን አላቸው። ከዚያም ረሱል ዝሙት የሚፈፅሙ ሰዎች ላይ ህግህን ተግባራዊ የሚያደርጉት አድርገኝ በማለት ተማፀኑና ሰላማዊ ህግ በሚያዘው መሰረት ተቀጥቅጦ እንዲገደል ሲያዙ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሙስሊም፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ مُصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيۡهِ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَمُهَيۡمِنًا عَلَيۡهِۖ فَٱحۡكُم
بَيۡنَهُم بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُۖ وَلَا تَتَّبِعۡ أَهۡوَآءَهُمۡ عَمَّا جَآءَكَ مِنَ ٱلۡحَقِّۚ لِكُلّٖ جَعَلۡنَا مِنكُمۡ شِرۡعَةٗ
وَمِنۡهَاجٗاۚ وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَجَعَلَكُمۡ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ وَلَٰكِن لِّيَبۡلُوَكُمۡ فِي مَآ ءَاتَىٰكُمۡۖ فَٱسۡتَبِقُواْ
ٱلۡخَيۡرَٰتِۚ إِلَى ٱللَّهِ مَرۡجِعُكُمۡ جَمِيعٗا فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ فِيهِ تَخۡتَلِفُونَ ﴿٤٨﴾ وَأَنِ ٱحۡكُم
بَيۡنَهُم بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ وَلَا تَتَّبِعۡ أَهۡوَآءَهُمۡ وَٱحۡذَرۡهُمۡ أَن يَفۡتِنُوكَ عَنۢ بَعۡضِ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ
إِلَيۡكَۖ فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَٱعۡلَمۡ أَنَّمَا يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُصِيبَهُم بِبَعۡضِ ذُنُوبِهِمۡۗ وَإِنَّ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلنَّاسِ
لَفَٰسِقُونَ ﴿٤٩﴾ أَفَحُكۡمَ ٱلۡجَٰهِلِيَّةِ يَبۡغُونَۚ وَمَنۡ أَحۡسَنُ مِنَ ٱللَّهِ حُكۡمٗا لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ﴿٥٠﴾

**48-50.** ከበፊቱ የነበረውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ አድርገን በአንተ ላይ ቁርኣንን አወረድን። እናም በመካከላቸው አላህ ባወረደው ህግ ብቻ ፍረድ። እውነቱ ከመጣልህ በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን አትከተል። ከናንተ መካከል ለሁሉም ህግንና መንገድን አደረግን። አላህ በፈለገ ኖሮ አንድ ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር። ግን በሰጣችሁ ሕግጋት ሊሞክራችሁ ነው (ለያንዳንዳችሁ መንገዶችን ያደረገው)። እናም በጎ ስራዎችን ለመስራት ተሽቀዳደሙ። የሁላችሁም መመለሻ ወደ አላህ ብቻ ነው። ከዚያ በእርሱ ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር እውነታ ይነግራችኋል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመካከላቸው አላህ ባወረደው ህግ ፍረድ እንጂ ፈላጎቶቻቸውን አትከተል። አላህ ወደ አንተ ካወረደው ከከፊሉ እንዳያሳስቱህ ተጠንቀቃቸው (ማለትን አወረድን)። ከውሳኔው እምቢ ብለው ቢዞሩም አላህ የሚሻው በከፊሉ ኃጢአታቸው ሊቀጣቸው መሆኑን እወቅ። ከሰዎቹ ብዙዎቹም አመፀኞች ናቸው። ለመሆኑ የመሀይምነትን* ፍርድ ይፈልጋሉን? በአላህ ለሚያረጋግጡ ሰዎች ሁሉ ከአላህ ይበልጥ ፍርዱ ያማረ ማን ነው?

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በአላህ ዘንድ በጣም የተጠሉ ሰዎች ሶስት ናቸው። እነርሱም:-

1. በተከበሩ ቦታዎች ውስጥ ሆኖ ከመልካም ባህሪያት አፈንጋጭ፤
2. በኢስላም ውስጥ ሆኖ በቅድመ ኢስላም ይተገበሩ የነበሩ ባሕሎች ተግባራዊ እንዲሆኑ የሚፈልግ የሆነ ሰው፤
3. የሰው ልጅ ነፍስ ካለ አግባብ ለማጥፋት የሚፈልግ ሰው»

ከመዐዱ ምዕራፍ (49) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ከዕብ ቢን ዑሰይድ፤ አብደላህ ቢን ሱሪያ፤ ሻስ ቢን ቀይስ የተባሉት አይሁዶች እርስ በራሳቸው ወደ ነብዩ (ﷺ) እየሄድን በእምነቱ እንፈትነው ብለው ሂደው ሙሐመድ ሆይ! እኛ የአይሁድ ምሁራን ነን። ታውቃለህ እኛን ከተከተልንህ አይሁድ

በሙሉ ተከተሉህ ማለት ነው ማንም አይንቅህም እኛ ከሰዎች ጋር ክርክር አለንና በአንተ እንዳኝ እንበላቸውና ለእኛ ፍረድልን እኛ ከዚያ በኋላ በአንተ እናምናለን ሲሏቸው ነብዩ (ﷺ) እምቢ ስላሉ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከመዐዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ **(24-49)** ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋናዋናዎቹ

1. አይሁድ ፈሪዎች መሆናቸውነና ከአላህ እና ከላካቸው መልዕክተኞቹ ጋር የነበራቸው ግንኙነት የተበላሸ እንደነበር፤
2. የወንጀለኞችን ተፈጥሮአዊ ስብዕና ሳይሆን የኃጢያት ተግባራቸውንና ጥፋታቸውን በሙሉ ልብ መጥላት እንደሚገባ፤
3. በወንጀለኞች ላይ በጥፋታቸው ምክንያት የአላህ ቁጣ ሲወርድባቸው እዝነትን ማሳየትና መራራት የተከለከለ መሆኑን፤
4. አላህን በሚወደው ነገር መቅረብ ተገቢ መንገድና ዘዴ መሆኑን፤
5. የምቀኝነትን ብልሹነት አስቀያሚ ምግባርነትን፤
6. መልካም ስራ ተቀባይነት የሚያገኘው በሙሉ ልብ ለአላህ ብቻ ተበሎ ሲሰራ ብቻ መሆኑን፤
7. ለመጀመሪያ ጊዜ የሰውን ነፍስ በማጥፋት (በመግደል) መጥፎ አርአያ የሆነው የአባታችን አደም ልጅ ቃቤል እንደነበር፤
8. የሰውን ልጅ አስከሬን (ሬሳ) መቅበር ብቸኛ አማራጭነቱ፤
9. ከሰው ልጆች የተሻለ ደረጃ የሚሰጠው ክቡር ሰው ማለት እጁን በሰው ላይ ከመሰንዘር ተቆጥቦ በግፊት የሞት ፅዋን እንዲቀምስ የሚገደደው (ተገዳይ) ሲሆን በግፍ ተነሣስቶ ነፍስ የሚያጠፋ (የሚገድል) ሰው ደግሞ መጥፎ ሰው መሆኑን፤
10. አላህ ለበኒ ኢስራኤል (የኢስራኤል ልጆች) ከስህተታቸው እንዲታረሙ በማሰብ የሰጠው ምክር ምን እንደሚመስል፤
11. የአይሁድ ማፈንገጥና መበላሸት በስህተት ወይም ባለማወቅ ሣይሆን በስሜት በመመራትና በትዕቢት መሆኑን፤
12. የአይሁድ ወንጀል በእጥፍ ድርብ የሚያስቀጣቸውና መልካም ስራቸውም እንዲሁ እጥፍ ድርብ ዋጋ እንዳለው፤
13. ቀማኛና ሽፍታ የሰውን ንብረትና ክብር በመዳፈሩ አላህ አሰቃቂ ቅጣት እንደደነገገለት፤
14. ለፈፀመው ወንጀል ምድራዊ ቅጣቱን ሣይቀበል በተውበት የተመለሰ ሰው የሚጠበቅበትን ግዴታ፤
15. አላህን መፍራት በእያንዳንዱ ሰው ላይ የተጣለ ግዴታ መሆኑን፤
16. በእምነት በመልካም ስራ ወደ አላህ ተወሱል ማድረግ የተፈቀደና ዱአን ተቀባይ ከሚያደርጉ ዘዴዎች የሚቆጠር መሆኑ፤
17. የቂያማ ቀን ቅጣት እጅግ ከባድና መራርነቱም የከፋ መሆኑ፤
18. ካፊሮችን (ከሓዲያንን) ያንን ሊጠቅም የሚችልና ከእሳት ቅጣት ነፃ ሊያወጣ የሚችል አማላጅነት ክፍያ ያሌለ መሆኑን፤
19. ሌባ የሰውን ንብረት በመዳፈሩ ምክንያት በምድር ላይ እያለ የሚወስድበት የቅጣት እርምጃ ዝርዝር ይዘት ምን እንደሚመሰልና ሌባ ሥርቆቱን ትቶ ንስሃ ተውባት ከገባ ተቀባይነት እንደሚያገኝ ሌላው ቀርቶ ለፍርድ ባለመቅረቡ ምክንያት ምድራዊ ቅጣተ ሳይፈፀምበት ተውበት ከገባ ተቀባይነት ያለው መሆኑንና ፍርድ አደባባይ ከቆመ በኋላ ግን ቅጣቱ ሣይፈፀምበት ተውበት ተቀባይነት የሌለው መሆኑን፤
20. የአላህን ውሳኔና ፍርድ ያለምንም ማንገራገር መቀበል ያለው ግዴታነት፤

21. ለሐዘን የሚያበቁትን በመራቅ የቅድሚያ ጥንቃቄ መውሰድ ተገቢ መሆኑን፤
22. ውሸትን መናገር ብቻ ሳይሆን የውሸት ንግግሮችን እያወቁ ማድመጡ እንኳን የተከለከለ መሆኑን፤
23. ነገሮችን ለመለወጥና ለማጠፍ የአላህን ቃል መቀያየር የተወገዘና ክልክልነቱም የፀና ወንጀል መሆኑን፤
24. ለሁሉም ክስተቶችና ውዝግቦች ቁርአንና ሀዲስን ተመርኩዞ ውሳኔን መስጠት ተገቢ መሆኑን፤
25. ፍርድን ለመስጠት ከቁርአንና ከሐዲስ ውጭ ያሉ ህግጋትን ማጣቀስና መጠቀም ለሙስሊሞች የማይፈቀድ መሆኑን፤
26. ሐቅን በመጣስ ስሜትን መከተል ለጥፋት የሚዳርግ አካሄድ መሆኑን በማመን ስሜትን ከመከተል መራቅ እንደሚገባ፤
27. ሕግጋት የመለያያቸውን አብይ ምክንያት ፈተናን የሚቋቋመውን ትክክለኛ አማኝ ለመለየት እንደሆነ፤
28. የዚህች አለም ፈተናዎች መንስኤ አላህን ያለ አግባብ ከመወንጀል የሚመነጭ መሆኑን እንማራለን።

۞يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُواْ ٱلۡيَهُودَ وَٱلنَّصَٰرَىٰٓ أَوۡلِيَآءَۘ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلِيَآءُ بَعۡضٖۚ وَمَن
يَتَوَلَّهُم مِّنكُمۡ فَإِنَّهُۥ مِنۡهُمۡۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ٥١ فَتَرَى ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم
مَّرَضٞ يُسَٰرِعُونَ فِيهِمۡ يَقُولُونَ نَخۡشَىٰٓ أَن تُصِيبَنَا دَآئِرَةٞۚ فَعَسَى ٱللَّهُ أَن يَأۡتِيَ بِٱلۡفَتۡحِ أَوۡ أَمۡرٖ
مِّنۡ عِندِهِۦ فَيُصۡبِحُواْ عَلَىٰ مَآ أَسَرُّواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۡ نَٰدِمِينَ ٥٢ وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَهَٰٓؤُلَآءِ
ٱلَّذِينَ أَقۡسَمُواْ بِٱللَّهِ جَهۡدَ أَيۡمَٰنِهِمۡ إِنَّهُمۡ لَمَعَكُمۡۚ حَبِطَتۡ أَعۡمَٰلُهُمۡ فَأَصۡبَحُواْ خَٰسِرِينَ ٥٣

**51-53.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፤ አይሁዶችንና ክርስቲያኖችን ረዳቶች አድርጋችሁ አትያዙ። ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸውና። ከናንተ ውስጥ እነርሱን ረዳቶቹ (ወዳጆቹ) የሚያደርጋቸው ሰው ሁሉ ከእነርሱ አንዱ አካል ነው። አላህ አመፀኞችን ህዝቦች አያቀናም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን በልቦቻቸው ውስጥ የንፍቅና በሽታ ያለባቸውን ሰዎች የጊዜ መለዋወጥ እንዳያገኘን እንፈራለን የሚሉ ሲሆኑ በነርሱ (አይሁዶችን ለመረዳት) ሲቻኮሉ ታያቸዋለህ። አላህ ድል መንሳትን ወይም ከእርሱ ዘንድ እነርሱን የሚያደክም የሆነን ነገር ሊያመጣና ከዚያ በነፍሶቻቸው ውስጥ በደበቁት ነገር ተፀፃቾች እንደሚሆኑ አረጋገጠ። እነዚያ በአላህ ያመኑ ሰዎች ሁሉ እነዚያ ከናንተ ጋር ነን ብለው የጠነከረ መሀላቸውን በአላህ የማሉት እነዚህ ናቸውን? ይላሉ። ስራዎቻቸውም ተበላሹ። ከሳሪዎችም ሆኑ።

ከመዐዱ ምዕራፍ (51-52) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ዑባዳት ቢን ሷሚት እኔ ብዙ አይሁዶች ወዳጆች አሉኝ እኔ ከአይሁድ ወዳጅነት ወደ አላህ ወደ መልዕክተኛው እሸሻለሁ ሲሉ አብደላህ ቢን ኡበይ ግን እኔ ግን ከአይሁድ ጋር ያለኝን ወዳጅነት አልሰረዘም። አጋጣሚዎችን ባለበት ጊዜ ነበር እነዚህ አናቅፅ የወረዱበት። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَن يَرۡتَدَّ مِنكُمۡ عَن دِينِهِۦ فَسَوۡفَ يَأۡتِي ٱللَّهُ بِقَوۡمٖ يُحِبُّهُمۡ
وَيُحِبُّونَهُۥٓ أَذِلَّةٍ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ أَعِزَّةٍ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ يُجَٰهِدُونَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَلَا يَخَافُونَ
لَوۡمَةَ لَآئِمٖۚ ذَٰلِكَ فَضۡلُ ٱللَّهِ يُؤۡتِيهِ مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ وَٰسِعٌ عَلِيمٌ ٥٤

**54.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከናንተ ውስጥ ከሃይማኖቱ ወደ ክህደት የሚመለስ ሰው ሁሉ አላህ በእርሱ ስፍራ የሚወዳቸውና የሚወዱትን በምዕምናን ላይ ትሁቶች፤ በከሓዲያን ላይ ሀያላን፤ የሆኑትንና በአላህ መንገድ የሚታገሉን የወቃሽን ወቀሳ የማይፈሩን ህዝቦች በእርግጥ ያመጣል። ይህ የአላህ ችሮታ ነው። ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል። አላህ ችሮታው ሰፊ ሁሉንም አዋቂ ነውና።

إِنَّمَا وَلِيُّكُمُ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱلَّذِينَ يُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَهُمۡ
رَٰكِعُونَ ٥٥ وَمَن يَتَوَلَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ فَإِنَّ حِزۡبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلۡغَٰلِبُونَ ٥٦

**55-56.** (አማኞች ሆይ)፣ ረዳታችሁ አላህና መልዕክተኛው እንደዚሁ እነዚያም በአላህ ያመኑት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነርሱ ማለት እነዚያ ሶላትን በደንቡ የሚሰግዱ እነርሱም (ለአምልኮ) የሚያጎነበሱ ሆነው ምጽዋትን የሚሰጡ ናቸው። አላህን፤ መልዕክተኛውንና እንደዚሁ እነዚያ በአላህ ያመኑትን ሰዎች የሚወዳጅ ሰው ሁሉ ከአላህ ቡድኖች ይሆናል። የአላህ ቡድኖች ደግሞ አሸናፊዎች እነርሱ ብቻ ናቸው።

ከመዐዱ ምዕራፍ (55-56) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:-ዐብደላህ ቢን ሰላም ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ በኒቁረይዛዎችና በኒነዲሮች እኛን ትተውናል ስለ አራራቁን ከአንተ ባልደረቦች ጋርም መቀመጥ አይቻልም በማለት አይሁዶች እያደረሱባቸው ያለውን በደል ሲነግሯቸው ይህ አንቀፅ ወርዶ አንቀፁን ለነብዩ (ﷺ) ለዐብደላህ ቢን ሰላም ሲያነቡለት አላህ የነብዩና (ﷺ) የአማኞችን ወደጅነት ወደናል አሉ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُواْ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ دِينَكُمۡ هُزُوٗا وَلَعِبٗا مِّنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ
ٱلۡكِتَٰبَ مِن قَبۡلِكُمۡ وَٱلۡكُفَّارَ أَوۡلِيَآءَۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٥٧ وَإِذَا نَادَيۡتُمۡ إِلَى
ٱلصَّلَوٰةِ ٱتَّخَذُوهَا هُزُوٗا وَلَعِبٗاۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ قَوۡمٞ لَّا يَعۡقِلُونَ ٥٨

**57-58.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከእነዚያ ከበፊታችሁ መጽሐፍን ከተሰጡትና ከእነዚያ ሃይማኖታችሁን ማላገጫና መጫወቻ አድርገው*[1] ከያዙት ከሐዲያን መካከል ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ። ትክክለኛ ምዕመናን

እንደሆናችሁ አላህን ብቻ ፍሩ። (ሙስሊሞች ሆይ!፣ ማንንም) ወደ ሶላት በጠራችሁ ጊዜ ጥሪዋን መሳለቂያና መጫዎቻ አድርገው ይይዟታል። ይህ እነርሱ የማያውቁ ህዝቦች በመሆናቸው*2 ነው።

✳1 ይህና መሰል የቁርኣን አናቅፅ በሃይማኖታችን ማላገጥ ምን ያህል የተኮነነና የተወገዘ መሆኑን ያመለክታል። እዚህ ላይ ሊጤን የሚገባው ነገር ቢኖር እነዚህ አባባሎች የጨዋታን አስፈላጊነትን ቢያንስ ቢያንስ የሚፈቅድ መሆኑን ይጠቁማሉ። ለምሳሌ ነብዩ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (ወርውሩ እኔ ከእናንተ ጋር ነኝ) ያሉት፣ እናታችን አዒሻ ሐበሻዎች ሲጫወቱ በነብዩ ተከልዬ እስኪበቃኝ እመለከት ነበር ያሉትና፣ ኡመር ቢንኸጣብ (ልጆቻቸውን ዋናና ውርወራ አስተምሯቸው) ብለዋል። ስለዚህ ኢስላም ጨዋታ ሙሉ በሙሉ የማይከለክል እና ገደብ ሲያልፍ ግን እንደሚከለክል ነው። የፈረስ ግልቢያ የሩጫ ውድድር፣ ከመፈቀድም አልፎ ተገቢ ነው።

✳2 አዛን ማለት የሶላት ወቅት መድረሱን ለማሳወቅና ሰዎችም ለመስገድ ወደ መስጊድ እንዲሰባሰቡ የሚደረግ ጥሪ ሲሆን ይዘቱም የሚከተለው ነው:- «አላሁ አክበር አላሁ አክበር፣ አላሁ አክበር አላሁ አክበር፣ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለልላህ፣ አሽሀዱ አን ላ ኢላሀ ኢልለልላህ፣ አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ፣ አሽሀዱ አንነ ሙሐመደን ረሱሉላህ፣ ሐይያ ዐለ ሶላህ፣ ሐይያ ዐለ ሶላህ፣ ሐይያ ዐለል ፈላሕ፣ ሐይያ ዐለል ፈላሕ፣ አላሁ አክበር አላሁ አክበር፣ ላኢላሀ ኢልለልላህ።

ኢቃማ ማለት ወደ ሶላቱ መግቢያ የሚደረግ ጥሪ ማለት ነው። ከአዛን ቃላት ምንም የሚለይ አይደለም ዳሩ ግን ሁለት ጊዜ ሲደጋገሙ የነበሩትን የአዛን ቃላቶች አንድ አንድ ጊዜ ብቻ ማድረግ ሲሆን በስተመጨረሻ «ከሐያይ ዐለል ፈላሕ» በኋላ «ቀድ ቃመቲ» ሶላቱ፣ ቀድ ቃመቲ ሰላህ» የሚለውን ሐረግ ሁለት ጊዜ ከደጋገመ በኋላ ቀሪውን ቃላት መጨመር ማለት ነው።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «ሰዎች ደውልንና እሳትን ወደ ሶላት ለመጥራት እንደምልክትነት አድርገው ጠቀሱ። በዚህም ንና ክርስቲያኖችን ጠቀሱ። ከዚያ በኋላ ቢላል ቃላቶቹን እየደጋገመ አዛን እንዲያደርግ እንዲሁም ለኢቃማህ ቃላቶቹን አንዳንድ ጊዜ እንዲል ታዘዘ።»

ከመዕዱ ምዕራፍ (57) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፣- ሪፋዓ ቢን ዘይድ እና ሱወይድ ቢን አል ሀሪስ የተባሉት ሰዎች በማስመሰል ከሙስሊሙ ጋር ይኖሩ የነበሩ አስመሳዮች ነበሩ አንዳንድ ሙስሊሞች የእነዚህ አስመሳዩችን ሳይረዱ ይወዷቸው ስለነበር እነዚህን ሙስሊሞች ለማስጠንቀቅ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ፣ ኢብኑል. ጀውዚ፣ ዋሒዲ ና እና ሱዩጢ)

ከመዕዱ ምዕራፍ (58) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የነብዩ (ﷺ) አዛን አድራጊ ሶላት ደርሶ አዛን ሲያደርግና ሙስሊሞች ለመስገድ በቆሙ ጊዜ አይሁዶችም እርስ በራሳቸው እናንተም ከእነሱ ጋር ቁሙና እነሱ ጋር ተመሳሰሉ። አፌዙባቸው ይሉ ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ቁርጡቢ)

قُلْ يَٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ هَلْ تَنقِمُونَ مِنَّآ إِلَّآ أَنْ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْنَا وَمَآ أُنزِلَ مِن قَبْلُ
وَأَنَّ أَكْثَرَكُمْ فَٰسِقُونَ ﴿٥٩﴾ قُلْ هَلْ أُنَبِّئُكُم بِشَرٍّ مِّن ذَٰلِكَ مَثُوبَةً عِندَ ٱللَّهِ ۚ مَن لَّعَنَهُ
ٱللَّهُ وَغَضِبَ عَلَيْهِ وَجَعَلَ مِنْهُمُ ٱلْقِرَدَةَ وَٱلْخَنَازِيرَ وَعَبَدَ ٱلطَّٰغُوتَ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ شَرٌّ مَّكَانًا
وَأَضَلُّ عَن سَوَآءِ ٱلسَّبِيلِ ﴿٦٠﴾

**59-60.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመጽሐፍ ባለቤቶች ሆይ፣ በአላህ ወደ እኛ በተወረደው ቁርኣንና በፊትም በተወረዱት ቅዱሳን መጽሐፍት ማመናችንና አብዛሀኞቻችሁ አመፀኞች መሆናችሁን እንጂ ሌላን ነገር ከእኛ ትጠላላችሁን? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ዘንድ ቅጣቱ ከዚህ ሁሉ የከፋን ነገር ልንገራችሁን? በላቸው። እርሱም አላህ የረገማቸውና በእነርሱም ላይ የተቆጣባቸው ሰዎች ናቸው። ከመካከላቸዉም የተወሰኑትን ዝንጀሮዎችና ከርከሮዎች ያደረጋቸው ጣዖትንም የተገዙ ሰዎች ሃይማኖት ነው። እነዚያ በጣም በከፋ ስፍራ ናቸው። ከቀጥተኛውም መንገድ በጣም የተሳሳቱ ናቸው።

ከመዐዱ (60) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-የተወሰኑ የአይሁድ ቡድኖች ወደ ነብዩ (ﷺ) ዘንድ በመምጣት ሙሐመድ ሆይ! አንተ የምታምንባቸው ነብያት እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ንገረን ሲሉ ጠየቋቸው። ነብዩም (ﷺ) እኔ በአላህና ወደ እኛ በወረደው በነብያት በኢብራሂም፣ በኢስማኢል፣ እያሉ የነብዩ ዒሳን ስም ሲያነሱ አይሁዳውያኑ እኛ እርሱን በነብይነት በፍፁም አናውቅም። ስለሆነም አንተ በእርሱ የምታምን ከሆነ በዱንያም ሆነ በአኼራ በጣም አነስተኛ እምነት ያለው ቡድን የአንተ ቡድን ነው ማለት ነው ያያዝከውም መንገድ የተሳሳተና መጥፎ ጎዳና ነው በማለታቸው የእነርሱን አባባል በመቃወም አላህ እኒህን አናቅፅ አወረደ። (ዋሒዲ፣ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَإِذَا جَآءُوكُمْ قَالُوٓاْ ءَامَنَّا وَقَد دَّخَلُواْ بِٱلْكُفْرِ وَهُمْ قَدْ خَرَجُواْ بِهِۦۚ وَٱللَّهُ أَعْلَمُ بِمَا
كَانُواْ يَكْتُمُونَ ﴿٦١﴾ وَتَرَىٰ كَثِيرًا مِّنْهُمْ يُسَٰرِعُونَ فِى ٱلْإِثْمِ وَٱلْعُدْوَٰنِ وَأَكْلِهِمُ ٱلسُّحْتَۚ
لَبِئْسَ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿٦٢﴾ لَوْلَا يَنْهَىٰهُمُ ٱلرَّبَّٰنِيُّونَ وَٱلْأَحْبَارُ عَن قَوْلِهِمُ ٱلْإِثْمَ وَأَكْلِهِمُ
ٱلسُّحْتَۚ لَبِئْسَ مَا كَانُواْ يَصْنَعُونَ ﴿٦٣﴾

**61-63.** (አማኞች ሆይ!) ወደ እናንተ በመጡ ጊዜ ከክህደት ጋር ሁነው የገቡ ከዚያ ከእርሱ ጋር ሁነው ብቻ በእርግጥ የወጡ ሲሆኑ ልክ እንደናንተ አምነናል ይላሉ። አላህ ያንን ይደብቁት የነበረውን ነገር ሁሉ ጠንቅቆ አዋቂ ነው።(መልዕክተኛችን መሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ ብዙዎቹን በኃጢአትና በበደል እርምንም የሆነ ለመብላት የሚጣደፉ ሲሆኑ ታያቸዋለህ። ይሰሩት የነበረው ሁሉ ነገር በጣም ከፋ! ቀሳውስቱና ሊቃውንቱ ከኃጢአት ንግግራቸውና እርምን ከመብላታቸው አይከለክሏቸውም ኖሯልን? ይሰሩት የነበረው ሁሉ በጣም ከፋ!

وَقَالَتِ ٱلْيَهُودُ يَدُ ٱللَّهِ مَغْلُولَةٌ ۚ غُلَّتْ أَيْدِيهِمْ وَلُعِنُوا۟ بِمَا قَالُوا۟ ۘ بَلْ يَدَاهُ مَبْسُوطَتَانِ يُنفِقُ
كَيْفَ يَشَآءُ ۚ وَلَيَزِيدَنَّ كَثِيرًا مِّنْهُم مَّآ أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ طُغْيَٰنًا وَكُفْرًا ۚ وَأَلْقَيْنَا بَيْنَهُمُ
ٱلْعَدَٰوَةَ وَٱلْبَغْضَآءَ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ ۚ كُلَّمَآ أَوْقَدُوا۟ نَارًا لِّلْحَرْبِ أَطْفَأَهَا ٱللَّهُ ۚ وَيَسْعَوْنَ فِى
ٱلْأَرْضِ فَسَادًا ۚ وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ ٱلْمُفْسِدِينَ ﴿٦٤﴾

**64.** አይሁዶች የአላህ እጅ የታሰረ ነው አሉ። እጆቻቸው ይታሰሩ። ባሉትም ነገር ይረገሙ። ጉዳዩ እነርሱ እንዳሉ አይደለም። የአላህ ሁለቱም እጆቹ* የተዘረጉ ናቸው። እንደፈለገ ይለግሳል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደው ቁርኣን ከእነርሱ መካከል ለብዙዎቹ ትዕቢትንና ክህደትን በእርግጥ ይጨምርባቸዋል። በአይሁዶች መካከል ጠብንና ጥላቻን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ አደረግን። ለጦር እሳትን ባቀጣጠሉ ቁጥር አላህ ያጠፋባቸዋል። በምድር ውስጥ ለማበላሸት ይሮጣሉ። አላህም አበላሾችን ሁሉ አይወድም።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የትንሳኤ ቀን አላህ ሁሉንም መሬቶች በአንድ እጁ በሌላው እጁ ደግሞ ሰባቱን ሰማያት ይይዝና «እኔ ንጉስ ነኝ» ይላል።

وَلَوْ أَنَّ أَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ ءَامَنُوا۟ وَٱتَّقَوْا۟ لَكَفَّرْنَا عَنْهُمْ سَيِّـَٔاتِهِمْ وَلَأَدْخَلْنَٰهُمْ جَنَّٰتِ
ٱلنَّعِيمِ ﴿٦٥﴾ وَلَوْ أَنَّهُمْ أَقَامُوا۟ ٱلتَّوْرَىٰةَ وَٱلْإِنجِيلَ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِم مِّن رَّبِّهِمْ لَأَكَلُوا۟ مِن
فَوْقِهِمْ وَمِن تَحْتِ أَرْجُلِهِم ۚ مِّنْهُمْ أُمَّةٌ مُّقْتَصِدَةٌ ۖ وَكَثِيرٌ مِّنْهُمْ سَآءَ مَا يَعْمَلُونَ ﴿٦٦﴾

**65-66.** የመጽሐፍ ባለቤቶች አላህን ባመኑና ከክህደት በተጠነቀቁ ኖሮ ከእነርሱ ኃጢአቶቻቸውን በእርግጥ ባበስንና የመጠቀሚያ ገነቶችን በእርግጥ ባስገባናቸው ነበር። እነርሱ ተውራትንና ኢንጂልን ከጌታቸው ወደ እነርሱ የተወረደውን መጽሐፍ በሰሩበት ኖሮ ከበላያቸውና ከእግሮቻቸው ስር በተመገቡ ነበር። ከእነርሱ ውስጥ ትክክለኛዎች* ህዝቦች አሉ። ከእነርሱ መካከል ብዙዎቹ ግን የሚሰሩት ነገር ከፋ!

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት ዐብደላህ ኢብኑ ሰላም የነብዩን ወደ መዲና መምጣት ወሬ ከሰማ በኋላ ወደ ነብዩ በመምጣት እንዲህ አላቸው። «ነብይ ካልሆነ በስተቀር ማንም የማያውቃቸው የሆኑ ሶስት ነገሮችን እጠይቅሃለሁ» እነርሱም፡-

1. በመጨረሻዋ ሰዓት የመጀመሪያ ምልክቶች ምንድን ናቸው?
2. የጀነት ሰዎች የሚመገቡት የመጀመሪያው ምግብ ምንድን ነው?
3. አንድ ልጅ ሲወለድ ወደ አባቱ ወይም ወደ እናቱ የማዘንበሉ ምስጢር ምንድን ነው?

ነብዩም (ﷺ) «አሁን ጅብሪል ስለነርሱ ነግሮኝ ነበር» አሉት። ኢብኑ ሰላምም «ጅብሪል ከመላዕክት መካከል ለጠላት የሆነ መልአክ ነው። አላቸው። እሳቸውም «ከመጨረሻዋ ሰዓት ምልክቶች የመጀመሪያው እሳት የሰው ልጆችን ከምስራቅ ወደ ምዕራብ አንድ ላይ ትሰበስባቸዋለች። የጀነት ሰዎች የሚመገቡት የመጀመሪያው ምግብ የአሳ ነባሪ ጉበት ነው። አንድ ልጅ ሲወለድ ወደ አባቱ ወይም እናቱ የማዘንበሉ ምስጢር የወንዱ ዘር ፈሳሽ ከሴቷ የዘር ፈሳሽ ከቀደመ ልጁ አባቱን ይመስላል። የሴቷ የዘር ፈሳሽ ከወንድ ዘር ፈሳሽ ከቀደመ ልጁ እናቱን ይመስል» አሉ። እሱም «ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባ አምላክ አለመኖሩን አንተን የአላህ መልዕክተኛ መሆንህን እመሰክራለሁ አለ። አያይዞም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የሚያስገርሙ ሕዝቦች ናቸው። ኢስላም መቀበሌን ሳያውቁ በፊት ስለኔ ጠይቃቸው» አላቸው። አይሁድ ወደ ነብዩ ሲመጡ ነብዩ «በናንተ መካከል ዐብደላህ ኢብኑ ሰላም ምን አይነት ሰው ነው?» ሲሉ ጠየቋቸው። አይሁዳዊያኑም «እርሱ ከኛ ውስጥ መልካምና የመልካም ሰዎች ልጅ ነው። እንዲሁም ከኛ የተሻለና ከኛ የሚሻሉት ሰዎች ልጅ ነው» በማለት መለሱላቸው። ነብዩም «ዐብደላህ ኢብኑ ሰላም ኢስላምን ቢቀበል ምን ይመስላችኋል?» ሲሉ አሁንም ን ጠየቋቸው። እነርሱም «አላህ ከዚህስ ይጠብቀው» አሏቸው። እሳቸው ጥያቄውን ደግመው ጠየቋቸው። አይሁዶችም ተመሳሳይ መልሳቸውን ደገሙላቸው። በዚህን ጊዜ ዐብደላህ ኢብኑ ሰላም ወደ ሰዎች በመውጣት «ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም፤ ሙሐመድም (ﷺ) በእርግጥ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን እመሰክራለሁ» አለ። አይሁዳዊያኑም ይህን ትዕይንት ከተመለከቱ በኋላ «እሱ ዐብደላህ ኢብኑ ሰላም ከኛ መካከል በጣም እርጉም የሆኑ ሰዎች ልጅ ነው» በማለት ክብሩን ማንኳሰስ ጀመሩ። እሱም ዐብደላህ ኢብኑ ሰላምም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኔም ይህን ነበር እፈራ የነበረው» አላቸው።

۞يَٰٓأَيُّهَا ٱلرَّسُولُ بَلِّغْ مَآ أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ ۖ وَإِن لَّمْ تَفْعَلْ فَمَا بَلَّغْتَ رِسَالَتَهُۥ ۚ وَٱللَّهُ
يَعْصِمُكَ مِنَ ٱلنَّاسِ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٦٧﴾ قُلْ يَٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَٰبِ لَسْتُمْ
عَلَىٰ شَىْءٍ حَتَّىٰ تُقِيمُوا۟ ٱلتَّوْرَىٰةَ وَٱلْإِنجِيلَ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْكُم مِّن رَّبِّكُمْ ۗ وَلَيَزِيدَنَّ كَثِيرًا
مِّنْهُم مَّآ أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ طُغْيَٰنًا وَكُفْرًا ۖ فَلَا تَأْسَ عَلَى ٱلْقَوْمِ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٦٨﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ
ءَامَنُوا۟ وَٱلَّذِينَ هَادُوا۟ وَٱلصَّٰبِـُٔونَ وَٱلنَّصَٰرَىٰ مَنْ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ وَعَمِلَ صَٰلِحًا
فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿٦٩﴾

**67-69.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን ቁርኣን አድርስ። ይህን ባትሰራ ግን የጌታህን መልዕክቱን አላደረስክም። (አድርስ) አላህ ከሰዎች ተንኮል ሁሉ ይጠብቅሃልና። አላህ ከሐዲያን ሕዝቦችን አያቀናምና። (መልዕክተኛች ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ የመጽሐፍ ባለቤቶች ሆይ፣ ተውራትን፤ ኢንጂልን እና ከጌታችሁ ወደ እናንተ የተወረደውን ቁርኣንን እስከምትሰሩባቸው ድረስ በምንም ላይ አይደላችሁም በላቸው። ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደው ቁርኣን ከእነርሱ ብዙዎቹን ትዕቢትንና ክህደትን በእርግጥ ይጨምርባቸዋል። በካሐዲያን ህዝቦች ላይ አትዘን። እነዚያ በአላህ ያመኑና፤ እነዚያም አይሁዳዊያን የሆኑ፤ ሳቢያኖችና ክርስቲያኖች ከእነርሱ መካከል

በአላህና በመጨረሻው ቀን በትክክል ያመኑና መልካምን ስራ የሰሩ ሰዎች ሁሉ በእነርሱ ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለውም አያዝኑምም።

ከመዐዱ ምዕራፍ (67) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- (ሀ) ነብዩ (ﷺ) በነብይነት ተመርጬ በተላኩኝ ጊዜ የተላከሁበት ጉዳይ እጅግ ከበደኝ እናም በጣም ተጨነኩኝ እንዲሁም የተላኩበትን ዓለማ የሚቃወሙና የሚያስተባብሉ ሰዎች እንደሚኖሩ በመገመትም በሀሳብ ተውጬ ሳለ ይህን የቁርኣን አንቀፅ በማውረድ ከትካዜ ገለገለኝ ማለታቸው ተዘግቧል። (ዋሒዲ፤ ኢብኑከሲር እና ኢብኑ-ልጀውዚ)

(ለ) የተወሰኑ አይሁድ ወደ ነብዩ (ﷺ) ዘንድ መጡና ተውራት ከአላህ የተወረደ መፅሐፍ መሆኑን ታምናለህን? በማለት ጠየቋቸው። ነብዩም (ﷺ) አዎን አምናለሁ አሏቸው። አይሁድም እኛም በእርሱ ብቻ እናምናለን ሌላውን የምትለውን አንቀበልም። በሌሎች እመኑ በምትለን መፅሐፍት አናምንም በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

(ሐ) ይህ አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ዘላን የጦር መሳሪያዉን መዞ ሙሐመድ ሆይ! አሁን ከእኔ ማን ያድንሃል ሲላቸው አላህ አሉት። ከዚያም እጁ ተንቀጠቀጠችና መሳሪያው ከእጁ አምልጦት ወደቀ። ከዚያም በብስጭት ራሱን ከግንድ ጋር እያጋጨ አናቱ ተበተነ። (ቲርሚዚ፤ ሃኪም እና ሱዩጢ።)

لَقَدْ أَخَذْنَا مِيثَٰقَ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ وَأَرْسَلْنَآ إِلَيْهِمْ رُسُلًا ۖ كُلَّمَا جَآءَهُمْ رَسُولٌۢ بِمَا لَا تَهْوَىٰٓ
أَنفُسُهُمْ فَرِيقًا كَذَّبُوا۟ وَفَرِيقًا يَقْتُلُونَ ﴿٧٠﴾ وَحَسِبُوٓا۟ أَلَّا تَكُونَ فِتْنَةٌ فَعَمُوا۟ وَصَمُّوا۟ ثُمَّ
تَابَ ٱللَّهُ عَلَيْهِمْ ثُمَّ عَمُوا۟ وَصَمُّوا۟ كَثِيرٌ مِّنْهُمْ ۚ وَٱللَّهُ بَصِيرٌۢ بِمَا يَعْمَلُونَ ﴿٧١﴾

**70-71.** የኢስራኤል ልጆች የጠበቀ ቃል ኪዳን በእርግጥ ያዝንባቸው። ወደ እነርሱም አያሌ መልዕክተኞችን ላክን። ነፍሶቻቸውን በማትወደው ነገር መልዕክተኛ በመጣላቸው ቁጥር ከፊሉን አስተባበሉ። ከፊሉንም ይገድላሉ። በእነርሱ ላይ ፈተና አለመኖሩዋን ጠረጠሩምና ታወሩ ደነቆሩም። ከዚያ አላህ ከእነርሱ ላይ ፀፀትን ተቀበለ። ከዚያ ከእነርሱ ብዙዎቹ እንደገና ታወሩ ደነቆሩ። አላህ የሚሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።

لَقَدْ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓا۟ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْمَسِيحُ ٱبْنُ مَرْيَمَ ۖ وَقَالَ ٱلْمَسِيحُ يَٰبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ
ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ رَبِّى وَرَبَّكُمْ ۖ إِنَّهُۥ مَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَقَدْ حَرَّمَ ٱللَّهُ عَلَيْهِ ٱلْجَنَّةَ وَمَأْوَىٰهُ ٱلنَّارُ ۖ
وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنْ أَنصَارٍ ﴿٧٢﴾ لَّقَدْ كَفَرَ ٱلَّذِينَ قَالُوٓا۟ إِنَّ ٱللَّهَ ثَالِثُ ثَلَٰثَةٍ ۘ وَمَا مِنْ إِلَٰهٍ إِلَّآ
إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ ۚ وَإِن لَّمْ يَنتَهُوا۟ عَمَّا يَقُولُونَ لَيَمَسَّنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنْهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٧٣﴾
أَفَلَا يَتُوبُونَ إِلَى ٱللَّهِ وَيَسْتَغْفِرُونَهُۥ ۚ وَٱللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٧٤﴾

**72-74.** እነዚያ አላህ እርሱ የመርየም ልጅ አልመሲህ ነው ያሉ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ በአላህ ካዱ። አል መሲህም አለ፡- የኢስራኤል ልጆች ሆይ፣ ጌታዬንና ጌታችሁን አላህን ተገዙ። እነሆ፣ በአላህ የሚያጋራ ሰው አላህ በእርሱ ላይ ገነትን በእርግጥ እርም አደረገ። መኖሪያውም እሳት ናት። ለበዳዩችም ምንም ረዳቶች የሏቸውም። እነዚያ አላህ የሶስት ሶስተኛ ነው ያሉ ሁሉ በእርግጥ በአላህ ካዱ ከአምላክም አንድ አምላክ ብቻ እንጂ ሌላ አምላክ የለም። ከሚሉትም ነገር ካልተከለከሉ እነዚያን የካዱትን ሁሉ አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል። (ለመሆኑ እንደነዚህ አይነቶች) ወደ አላህ አይመለሱምን ምህረትን አይለምኑትምን? አላህ መሀሪና አዛኝ ነው።*

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከናንተ መካከል አንዱ ግመሉ በርሃ ላይ ሳለ ጠፍቶት ካገኘው በኋላ ከሚያገኘው ደስታ በበለጠ አላህ አንድ ባሪያው በሚያደርገው ንሰሃ ተደሳች ነው።»

مَّا ٱلْمَسِيحُ ٱبْنُ مَرْيَمَ إِلَّا رَسُولٌ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِهِ ٱلرُّسُلُ وَأُمُّهُۥ صِدِّيقَةٌ ۖ كَانَا يَأْكُلَانِ ٱلطَّعَامَ ۗ ٱنظُرْ كَيْفَ نُبَيِّنُ لَهُمُ ٱلْـَٔايَـٰتِ ثُمَّ ٱنظُرْ أَنَّىٰ يُؤْفَكُونَ ﴿٧٥﴾ قُلْ أَتَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَمْلِكُ لَكُمْ ضَرًّا وَلَا نَفْعًا ۚ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٧٦﴾

**75-76.** የመርየም ልጅ አልመሲህ ከበፊቱ መልዕክተኞች የቀደሙት መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለም። እናቱም በጣም እውነተኛ ናት። ሁለቱም ምግብን የሚበሉ ነበሩ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አናቅፅን ለከሐዲያን እንዴት እንደምናብራራና ከዚያም እነርሱ ከእውነት እንዴት እንደሚመለሱ ተመልከት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ፣) ከአላህ ሌላ ለእናንተ መጉዳትንና መጥቀምን የማይችልን ትገዛላችሁን? አላህ እርሱ ሰሚና አዋቂ ነው በላቸው።

قُلْ يَـٰٓأَهْلَ ٱلْكِتَـٰبِ لَا تَغْلُوا۟ فِى دِينِكُمْ غَيْرَ ٱلْحَقِّ وَلَا تَتَّبِعُوٓا۟ أَهْوَآءَ قَوْمٍ قَدْ ضَلُّوا۟ مِن قَبْلُ وَأَضَلُّوا۟ كَثِيرًا وَضَلُّوا۟ عَن سَوَآءِ ٱلسَّبِيلِ ﴿٧٧﴾ لُعِنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنۢ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ عَلَىٰ لِسَانِ دَاوُۥدَ وَعِيسَى ٱبْنِ مَرْيَمَ ۚ ذَٰلِكَ بِمَا عَصَوا۟ وَّكَانُوا۟ يَعْتَدُونَ ﴿٧٨﴾ كَانُوا۟ لَا يَتَنَاهَوْنَ عَن مُّنكَرٍ فَعَلُوهُ ۚ لَبِئْسَ مَا كَانُوا۟ يَفْعَلُونَ ﴿٧٩﴾

**77-79.** (መልዕክተኞች ሙሐመድ ሆይ)፣ እናንተ የመጽሐፍ ባለቤቶች ሆይ፣ በሃይማኖታችሁ ከእውነት ሌላ ወሰንን አትለፉ። በፊትም በእርግጥ የተሳሳቱትንና ብዙዎቹን ህዝቦች ያሳሳቱትን ከቀጥተኛው መንገድም አሁን

የተሳሳቱ ህዝቦች ከንቱ ዝንባሌዎች (ስሜቶች) አትከተሉ በላቸው። ከኢስራኤል ልጆች መካከል እነዚያ በአላህ የካዱ ክፍሎች በዳውድና በመርየም ልጅ በዒሳ ምላስ ተረገሙ። ይህ የሆነው የአላህን ትዕዛዝ በመጣሳቸውና ወሰን የሚያልፉ በመሆናቸው ነው። ይሰሩት ከነበረው መጥፎ ነገር አይከላከሉም ነበር። ይሰሩት የነበረው ነገር በእርግጥ ከፋ፣ ✴

✴ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ከእስራኤላውያን ሕዝቦች መካከል ለምጥ ያለበትን፤ ዓይነ. ስውር የሆነንና ራሰ በራ የሆነን ሶስት ሰዎች ለመፈተኝ ፈልጎ መልአክ ወደነርሱ ላከ። መልአኩ ወደ ለምጣሙ ሄደና «በአንተ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነን ነገር ምንድ ነው?» ሲሉ ጠየቀው። ሰውየውም«ሰዎች በዚህ ሁኔታዬ ስለተጠየፉኝ ውብ ፊት ቀለምና ውብ ቆዳ እንዲኖረኝ ነው» በማለት መለሰለት። መልአኩም ፊቱን ዳሰሰለትና ለምጡ ጠፋለት። በምትኩም የፊት ቀለምና ውብ ቆዳ ተደረገለት። መልአኩም «በአንተ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነው ንብረት ምንድ ነው?» ሲል ጠየቀው። ሰውየውም «ሴት ግመል» ሲል መለሰ። እዚህ ላይ ራሰ በራው ሰውየ ነውን? ወይስ ይህ ለምጥ ያለበት ሰውዬ ግመል ወይም ላም የጠየቀው በሚለው ላይ አቡ ሁረይራህ ተጠራጥረዋል። ለሰውዬው እርጉዝ ሴት ግመል ተሰጠውና መልአኩ «አላህ ይህችን ይባርክልህ» አለውና ወደ ራስ በራው ሰውዬ ሄደ። «ባንተ ዘንድ በጣም ተወጃጅ የሆነው ነገር ምንድን ነው? ሲል ጠየቀው። «ሰዎች በዚህ ሁኔታዬ በጣም እየተጠየፉኝ ስለሆነ ውብ ፀጉር ኖሮኝ ይህ ራስ በራዬ እንዲጠፋልኝ ነው። በማለት መለሰለት። ውብ ፀጉርም ተሰጠው። አሁንም መልአኩ «ባንተ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነው ንብረት ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው። ሰውዬውም «ላም ነው» ሲል መለሰ። እርጉዝ የሆነች ላም ተሰጠውና መልአኩ «አላህ ይህችን ይባርክልህ» ብሎት ወደ ዓይነ. ስውሩ ሄደ። «ባንተ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነው ነገር ምንድን ነው?» ሲል እሱንም ጠየቀው። «ሰዎችን እንድንመለከትበት አላህ የአይን ብርሃኔን እንዲመልስልኝ ነው» ሲል መለሰ። መልአኩም አይኖቹን ዳበሰለትና ተፈወሰ። መልአኩም ቀጠል አድርጎ «ባንተ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የሆነው ንብረት ምንድን ነው?» ሲል ጠየቀው። ዓይነ. ስውሩም «ወላድ በግና ፍየል ነው» አለው። ወላድ የሆነች ሴት ፍየል ሰጠው። ሁሉም የተሰጧቸውን እንስሳት ተዋልደው የመጀመሪያ አንድ ሸለቆ የሚሞሉ በግና ፍየሎች አፈሩ። መልአኩ በፊት የተመሰለበትን ገፅታና ይዘት በመቀየር ለምጥ ወደነበረበት ሰውዬ በመምጣት «በመንገድ ላይ ስንቅ ያለቀበት ሚስኪን ነኝና ከአላህና ካንተ በስተቀር ዛሬ የሚረዳኝ የለም። ይህ ውብ የፊት ቀለም፤ ውብ ቆዳና ንብረት በሰጠህ ጌታ ወደ ጉዞዬ መዳረሻ የምታግዝበት አንድ ግመል እንድትሰጠኝ እጠይቅሃለሁ አለው። ሰውዬውም «ብዙ ኃላፊነቶች አለብኝ (ስለዚህ ልሰጥህ አልችልም። «አለው። መልአኩም «በእርግጥ የማውቅህ መሰለኝ። ሰዎች የሚጠየፉህ ለምጥ ያለብህ ሰው አልነበርክምን? እንዲሁም ድሃ ሆነህ አላህ ገንዘብ የሰጠህ አይደለህምን? «ሲል ጠየቀው። «ሰውየውም ከአያት ቅድመ አያቶቼ የወረስኩት ንብረት ነው» ሲል መለሰለት። መልአኩም «ውሸተኛ ከሆንክ ግን አላህ ወደነበርክበት ሁኔታ ይመልሰህ» ብሎት ወደ ራሰ በራው ሄደና ለለምጣሙ ሰው የጠየቀውን ሲጠይቀው ራሰ በራውም ሰው ለምጣሙ ሰው የመለሰውን አይነት መልስ ሰጠው። መልአኩም ውሸተኛ ከሆንክ አላህ ወደ ነበርክበት ይመልስህ «ብሎት» ወደ አይ. ስውሩ ሄደ። «ስንቅ ያለቀብኝ መንገደኛ ምስኪን ነኝ ከአላህና ከአንተ በስተቀር ዛሬ የሚረዳኝ የለም። አይኖችን በመለሰልህ ጌታህ ይሁንብኝ ለጉዞዬ መዳረሻ የምትሆነኝ አንዲት ፍየል ስጠኝ «አለው»። አይነስውሩም «በእርግጥ አይነ. ስውር ነበር፤ አላህ የአይኖቼን ብርሃን መለሰልኝ። ደሃም ነበርኩ ሀብታም አደረገኝ። ስለዚህ የፈለግከውን ያህል ውሰድ። በአላህ እምላለሁ የወሰድካቸውን ወስደህ ለአላህ ስትል በተውካቸው አላመሰግንም። «አለው»። መልአኩም «ንብረትህን ያዝ»። አላህ ሶስታችሁንም ፈትኗችኋል። አላህ በአንተ ሲደሰት ሁለቱን ጓደኞችህን ግን ተቆጥቶባቸዋል«አለው።»

تَرَىٰ كَثِيرًا مِّنْهُمْ يَتَوَلَّوْنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ۚ لَبِئْسَ مَا قَدَّمَتْ لَهُمْ أَنفُسُهُمْ أَن سَخِطَ ٱللَّهُ
عَلَيْهِمْ وَفِى ٱلْعَذَابِ هُمْ خَٰلِدُونَ ﴿٨٠﴾ وَلَوْ كَانُوا۟ يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلنَّبِىِّ وَمَآ أُنزِلَ إِلَيْهِ مَا
ٱتَّخَذُوهُمْ أَوْلِيَآءَ وَلَٰكِنَّ كَثِيرًا مِّنْهُمْ فَٰسِقُونَ ﴿٨١﴾

**80-81.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ መካከል ብዙዎቹን ከእነዚያ በአላህ ከካዱት ሰዎች ጋር ሲወዳጁ ታያለህ። በእነርሱ ላይ አላህ የተቆጣባቸው በመሆኑ ለእነርሱ ነፍሶቻቸውን ያስቀደሙት ስራ በጣም ከፋ፤ እነርሱ በቅጣት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። በአላህ በነብዩና ወደ እነርሱ በተወረደው ቁርኣን የሚያምኑ በሆኑማ ኖሮ ወዳጆች አድርገው ባልያዟቸው ነበር። ግን ከእነርሱ ብዙዎቹ አመፀኞች ናቸው።

**ከመዐዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (51-81) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. አይሁድን፤ ነሳራዎችን፤ እንዲሁም ከሓዲያን አጠቃላይ ከትክክለኛ እምነት ያፈነገጡ ሰዎችን በሙሉ ልብ ተብሎ ወዳጅነትን ከእነሱ ጋር መመስረት የተከለከለ መሆኑን፤
2. አቡበከር ሲዲቅ አላህ ዘንድ ያላቸው ክብርና ማዕረግ ከፍተኛነት፤
3. አላህን በሙሉ ልብ መውደድ ምእመናን መተናነስና ክብር መስጠት በከሓዲያን ላይ እውነትን አጥብቆ መያዝ በእውነት ላይ ፅኑ ሆኖ መኖር ኢስላማዊ ተግባር መሆናቸውን በዚህም ምክንያት የሚመጡ አሉባልታዎች በትዕግስት ማሳለፍ አላህ ዘንድ የሚያሰጠው ክብርና ምንዳ ከፍተኛ መሆኑ፤
4. ሰላት፤ ዘካና የአላህን ፍራቻ በልብ ውስጥ ማስገኘት ተወዳጅና ተፈላጊ ከሆኑ ኢስላማዊ ድንጋጌዎች መሆናቸውን፤
5. አላህና ነብዩን (ﷺ) እንዲሁም ትክክለኛ አማኞችን ማፍቀር (ወዳጅ ማድረግ) የበላይነትን ለመጨበጥ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነና ድልን እንደሚያጎናፅፍ፤
6. አይሁድም ሆነ ክርስቲያኖች እርስ በእርሳቸው ተደጋጋፊዎች እንደሆኑ፤
7. ሁለቱም ቡድኖች በሙስሊሞች ጉዳይ ላይ አንድ መሆናቸውን፤
8. ሙስሊም ሆኖ ከእነሱ ጋር ወዳጅነትን የፈጠረ ሰው በእምነቱ ላይ ችግር እንደሚያስጋው፤
9. ከአስመሳዮች ምልክት አይሁድንና ክርስቲያኖችን መቅረብ መሆኑን፤
10. አስመሳዮች ካፊሮችን የሚጠጉበት ምክንያት ምን እንደሆነ፤
11. አይሁዶችንና ነሣራዎች ባጠቃላይ ካፊሮችን በወዳጅነት መያዝ የተከለከለ ከመሆኑ ጋር በተለይ በሙስሊሞች ላይ ጥቃትን ከሚሰነዝሩና ከሚያሰቃዩና ግፈኛ ከሆኑት ካፊሮች ጋር ወዳጅነትን መመስረት እጅግ የተወገዘ መሆኑን፤
12. የአይሁድ ሥነ ምግባር በብልሹ ባህርያት የተገነባ መሆኑን፤
13. አይሁድ በዚያች በምድራዊ ዓለም ቆይታቸው ከህዝቦች በሙሉ በስህተት ጎዳና ላይ የሚራመዱና በቂያማ (በትንሳኤ) እለትም ውርደትና ቅጣት የሚጠብቃቸው ሕዝቦች መሆናቸውን፤
14. ከነብዩ ጊዜ አንስቶ የአስመሳዮች (አስመሳዮች) መነሻ አይሁድ እንደነበሩ፤

15. አይሁድ ወንጀልን በመስራታቸው የማያፍሩ ደንታ ቢሶች እንደሆኑ፤
16. አዋቂዎች የአላህ ህግ ቢጣስ በዝምታ መመልከቱ የሚያስጠይቃቸው መሆኑን፤
17. አላህን የእርሱ ባልሆነና ለእርሱ በማይገባ ባህርያት መግለፅ የተከለከለ መሆኑን፤
18. ከአላህ መልካም መግለጫዎችና ባህርያት መሀከል ሁለት እጆች ያሉት የሚለው መሆኑን፤
19. አይሁድና ክርስቲያኖች እርስ በራሳቸው የማይስማሙ በጠላትነት የሚተያዩ መሆናቸውን፤
20. የአይሁድ የዘወትር ምኞት ምድርን ማበላሸትና ፈሣድን (ብልሹነትን) መጨመር መሆኑን፤
21. የመፅሐፉ ሰዎች በነብዩ መልዕክተኙነት ካመኑ ክብርን እንደሚያገኙ የጀነት ተድላ እንደሚጎናፀፉ፤
22. ነብያት የተላኩበትን አቢይ ምክንያቶች ለመተግበርና የተላኩበትን አላማ ለመፈፀም ግዴታ የተጣለባቸው መሆኑን፤
23. ነብዩ (ﷺ) ይህንን ግዴታ በተገቢ ሁኔታ የፈፀሙ ኃላፊነታቸውንም የተወጡ መሆናቸውን፤
24. በነብዩ (ﷺ) መልዕክተኛነት ያመኑት ብቻ ሲቀሩ የመፅሐፍ ሰዎችም ቢሆኑ በሙሉ በከሃዲነት እንደሚፈረጁ፤
25. ሞገደኞችንና ትቢተኞችን ለማሳመን ማስረጃን መደርደር ምንም ጠቀሜታ እንደሌለው፤
26. እምነት በተግባር ካልተተረጎመና በመልካም ሥራ ካልታጀበ አምኛለሁ ብሎ መመፃደቅ ብቻውን አማኝ እንደማያሰኝ፤
27. ነብዩ ከስህተት የጠሩ ስህተት ውስጥም እንዳይወድቁ የአላህ ጥበቃና ከለላ ያላቸው መልዕክተኛ መሆናቸውን፤
28. የኢስራኤል ልጆች ታሪክ በአመፅና በትዕቢት የተሞላ እንደነበር ማጋለጥ፤
29. አላህ የኢስራኤል ልጆችን ጥፋታቸው ተደጋጋሚ መሆኑን እየተረዳ መጠነ ሰፊ ውለታን እንደዋለላቸው፤
30. አል-መሲህ የአላህ ልጅ ነው የሚሉት ከሓዲያን መሆናቸውን፤
ዒሣ የአላህ ልጅ ሣይሆኑ የእርሱ መልዕክተኛና ቅን አገልጋይ ባሪያው መሆናቸውን፤
31. በአላህ እያጋራ ተውበት (ንስሀ) ሣይገባ ሞት የቀደመው ሰው ጀነትን በፍፁም እንደማያገኝ፤
32. አምላክነት ለሶስት ወገኖች የሚሰጥ ሳይሆን አምላክነት ለአላህ ብቻ የሚገባው መሆኑን፤
33. ዒሣ እና እናቱ መርየም የአምላክነት ባህሪም ሆነ ድርሻ የሌላቸው የእርሱ ምርጥ አገልጋዮችና ባሪያ የነበሩ መሆናቸውን፤
34. ነሣራዎች ከክህደታቸው መመለስ ከፈለጉ የተውበት በሩ ያልተዘጋባቸው መሆኑን፤
35. ከአላህ ውጭ ማንኛውንም አካል አምላክ አድርጎ የያዘ ሰው የተወገዘ መሆኑን፤
36. የእምነት አካሄድ መለወጥ ድንጋጌዎችን ማጋነን አዳዲስ ፈሊጥ በማምጣት ስሜትን መከተል የተከለከለ መሆኑን፤
37. ወንጀልን መዳፈር ድንበርን በማለፍ ሕግጋትን መጣስ ለከፍተኛ ምድራዊና አኼራዊ ኪሣራ እንደሚዳርግ፤
38. ወንጀሎች ሲስፋፉ በዝምታ መመልከት ለወንጀሉ መሠራጨት አስተዋፅኦ በመሆኑ መከላከል ግዴታ መሆኑን፤
39. የክህደት አራማጆችን ማፍቀርና ወዳጁ አድርጎ መያዝ የክህደት ምልክት መሆኑን ማወቅ እንደሚያሻ እንማራለን።

۞لَتَجِدَنَّ أَشَدَّ ٱلنَّاسِ عَدَٰوَةً لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱلْيَهُودَ وَٱلَّذِينَ أَشْرَكُواْۖ
وَلَتَجِدَنَّ أَقْرَبَهُم مَّوَدَّةً لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱلَّذِينَ قَالُوٓاْ إِنَّا نَصَٰرَىٰۚ
ذَٰلِكَ بِأَنَّ مِنْهُمْ قِسِّيسِينَ وَرُهْبَانًا وَأَنَّهُمْ لَا يَسْتَكْبِرُونَ ﴿٨٢﴾

82. *(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አይሁዶችንና እነዚያ በአላህ ያጋሩት ሰዎች ለእነዚያ በአላህ ለአመኑት ጠላትነት ከሌሎች ሰዎች ሁሉ የበረቱ ሆነው ታገኛቸዋለህ። ከእነርሱ መካከል እነዚያ እኛ ክርስቲያኖች ነን ያሉትን ደግሞ ለእነዚያ በአላህ ለአመኑት በወዳጅነት ይበልጥ የቀረቧቸው ሆነው ታገኛቸዋለህ። ይህ የሆነው ከእነርሱ መካከል ቀሳውስትና መነኮሳት በመኖራቸውና እነርሱም የማይኮሩ በመሆናቸው ነው።

* ክፍል ሰባት

وَإِذَا سَمِعُواْ مَآ أُنزِلَ إِلَى ٱلرَّسُولِ تَرَىٰٓ أَعْيُنَهُمْ تَفِيضُ مِنَ ٱلدَّمْعِ مِمَّا عَرَفُواْ مِنَ ٱلْحَقِّۖ
يَقُولُونَ رَبَّنَآ ءَامَنَّا فَٱكْتُبْنَا مَعَ ٱلشَّٰهِدِينَ ﴿٨٣﴾ وَمَا لَنَا لَا نُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَمَا جَآءَنَا مِنَ
ٱلْحَقِّ وَنَطْمَعُ أَن يُدْخِلَنَا رَبُّنَا مَعَ ٱلْقَوْمِ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٨٤﴾

83-84. ወደ መልዕክተኛው የተወረደውን ቁርኣን በሰሙ ጊዜ እውነቱን ከመረዳታቸው የተነሳ ዓይኖቻቸው እንባን ሲያፈሱ ታያለህ። ጌታችን ሆይ! በአንተ አምነናል። ከመስካሪዎችም ጋር ፃፈን ይላሉ። ጌታችን ከመልካም ሰሪዎች ጋር ገነትን ሊያስገባን የምንከጅል ስንሆን በአላህና ከእርሱ በመጣልን እውነት ነገር ሁሉ የማናምንበት ምን ምክንያት አለን (ይላሉ)።

فَأَثَٰبَهُمُ ٱللَّهُ بِمَا قَالُواْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ وَذَٰلِكَ جَزَآءُ
ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٨٥﴾ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَآ أُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلْجَحِيمِ ﴿٨٦﴾

85-86. እናም ባሉት ምክንያት አላህ በስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶችን በውስጣቸው ዘወታሪዎች ሲሆኑ መነዳቸው። ይህ የበጎ ሰሪዎች ሁሉ ዋጋ ነውና። እነዚያም በአላህ የካዱና በአንቀፆቻችን ያስተባበሉ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው።

ከመዐዱ ምዕራፍ ከ (82-86) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሀገራችን ንጉስ ነጃሺና ወደ እርሱ በመጡት በባልደረቦቹ እና እንደዚሁም ነጃሺ ወደ ነብዩ (ﷺ) ልከዋቸው በነበሩ ሰላሳ ሰዎች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ል-ጀውዚ፤ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُحَرِّمُواْ طَيِّبَـٰتِ مَآ أَحَلَّ ٱللَّهُ لَكُمْ وَلَا تَعْتَدُوٓاْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ
ٱلْمُعْتَدِينَ ﴿٨٧﴾ وَكُلُواْ مِمَّا رَزَقَكُمُ ٱللَّهُ حَلَـٰلًا طَيِّبًا ۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِىٓ أَنتُم بِهِۦ مُؤْمِنُونَ ﴿٨٨﴾

**87-88.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህ ለእናንተ የፈቀደላችሁን ጣፋጮች በራሳችሁ ላይ እርም አታድርጉ። ወሰንንም አትለፉ። አላህ ወሰን አላፊዎችን ሁሉ አይወድምና። (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይ የተፈቀደ ጣፋጭ ሲሆን ብሉ ያንን ያመናችሁበትን አላህን ብቻ ፍሩ።

لَا يُؤَاخِذُكُمُ ٱللَّهُ بِٱللَّغْوِ فِىٓ أَيْمَـٰنِكُمْ وَلَـٰكِن يُؤَاخِذُكُم بِمَا عَقَّدتُّمُ ٱلْأَيْمَـٰنَ ۖ
فَكَفَّـٰرَتُهُۥٓ إِطْعَامُ عَشَرَةِ مَسَـٰكِينَ مِنْ أَوْسَطِ مَا تُطْعِمُونَ أَهْلِيكُمْ أَوْ كِسْوَتُهُمْ
أَوْ تَحْرِيرُ رَقَبَةٍ ۖ فَمَن لَّمْ يَجِدْ فَصِيَامُ ثَلَـٰثَةِ أَيَّامٍ ۚ ذَٰلِكَ كَفَّـٰرَةُ أَيْمَـٰنِكُمْ إِذَا حَلَفْتُمْ ۚ
وَٱحْفَظُوٓاْ أَيْمَـٰنَكُمْ ۚ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمْ ءَايَـٰتِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴿٨٩﴾

**89.** (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህ በማሃላዎቻችሁ መካከል በውድቁ አይዛችሁም። ባሰባችሁበት መሀላ ግን ይይዛችኋል። (መሀላዎችን ባፈረሳችሁ) ጊዜ ማስረገዋው ቤተሰቦቻችሁን ከምትመግቡት ከመካከለኛው ምግብ ለአስር ሚስኪኖች ማብላት ወይም እነርሱን ማልበስ ወይም የአንዲትን ባሪያ ጫንቃን ነፃ ማውጣት ነው። ከተባሉት አንዱን ያለገኘም ሰው ሶስት ቀኖችን መፆም ብቻ ነው። ይህ በማላችሁና መሀላዎቻችሁን ባፈረሳችሁ ጊዜ ማስረገዋ* ነው። መሀላዎቻችሁንም ጠብቁ። እንደዚሁ አላህ ለእናንተ አንቀፆችን ያብራራል። እናንተም ልታመሰግኑት ይከጀላልና።

✴ ከመዐዱ ምዕራፍ ከ (87-89) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- አንድ ሰውዬ ወደ ነብዩ መጣና እኔ ስጋ ስበላ ፆታዊ ስሜቴ ስለሚነሳሳ ስጋን መብላት በራሴ ላይ ሐራም አድርጊያለሁ በማለቱ ይህ አንቀፅ ወረደና የያዘው አቋም በተመለከተ ብይን ሰጠ። (ዋሒዲ)

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّمَا ٱلْخَمْرُ وَٱلْمَيْسِرُ وَٱلْأَنصَابُ وَٱلْأَزْلَـٰمُ رِجْسٌ مِّنْ عَمَلِ ٱلشَّيْطَـٰنِ
فَٱجْتَنِبُوهُ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٩٠﴾ إِنَّمَا يُرِيدُ ٱلشَّيْطَـٰنُ أَن يُوقِعَ بَيْنَكُمُ ٱلْعَدَٰوَةَ وَٱلْبَغْضَآءَ
فِى ٱلْخَمْرِ وَٱلْمَيْسِرِ وَيَصُدَّكُمْ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ وَعَنِ ٱلصَّلَوٰةِ ۖ فَهَلْ أَنتُم مُّنتَهُونَ ﴿٩١﴾

**90-91.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! የሚያሰክር መጠጥ፤ የቁማር ጫዎታ፤ ጣዖታትም መገዛት እና አዝላምም*[1] ከሰይጣን ስራ የሆነ እና እርኩስ ተግባር ነው። እናም ከጀሀነም እሳት ትድኑ ዘንድ ራቁት። ሰይጣን የሚፈልገው

በሚያሰክር መጠጥና በቁማር አማካኝነት በመካከላችሁ ጠብንና ጥላቻን ሊጭርና አላህን ከማውሳትና ከስግደት ሊያግዳችሁ ብቻ ነው። ታዲያ እናንተ ከእነዚህ ነገሮች ተከልካዩች ናችሁን?*2 (ተከልከሉ)

*1 የሚመለኩ ነገሮች ኀበድኖች፤ መቃብሮች... የመሳሰሉት

*2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ከኔ ህዝቦች መካከል ዝሙትን፤ የሐር ልብስን፤ አስካሪ መጠጥንና የሙዚቃ መሳሪያዎችን የሚፈቅዱ ሰዎች (በመጨረሻ ዘመን) በእርግጥ ይኖራሉ። ከነርሱ መካከልም ከተራራ በኩል ተቀምጠው የነርሱ ከብት ጠባቂ የሆነ ሰው የነርሱን ከብቶች ወደነርሱ ይዞ በመምጣት ስለአንዳች ነገር ይጠይቃቸዋል። እነርሱም «ነገ ተመለስልን» ይሉታል። አላህ እነርሱን በለሊት ያጠፉቸዋል ተራራውንም በነርሱው ላይ ያወድመዋል። የተቀሩትን ደግሞ ወደ ዝንጀሮነትና ወደ አሳማነት ይለውጣቸዋል። በዚህ ሁኔታቸው እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ በምድር ላይ ይቆያሉ»

وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَٱحۡذَرُواْۚ فَإِن تَوَلَّيۡتُمۡ فَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّمَا عَلَىٰ رَسُولِنَا ٱلۡبَلَٰغُ
ٱلۡمُبِينُ ٩٢ لَيۡسَ عَلَى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ جُنَاحٞ فِيمَا طَعِمُوٓاْ إِذَا مَا ٱتَّقَواْ
وَّءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ ثُمَّ ٱتَّقَواْ وَّءَامَنُواْ ثُمَّ ٱتَّقَواْ وَّأَحۡسَنُواْۚ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٩٣

**92-93.** (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህን ብቻ ተገዙ። መልዕክተኛውንም ታዘዙ። ተጠንቀቁ። ብትሸሹም በመልዕክተኛችን ላይ ያለበት በግልፅ መልዕክቱን ማድረስ ብቻ መሆኑን እወቁ። በእነዚያ በአላህ ባመኑትና በጎ ስራዎችን በሰሩት ሰዎች ላይ (ክህደትን) ከተጠነቀቁና ለአላህ መልካም ስራወችንም በሰሩ ከዚያም (የሚያሰክርንና ቁማርን) ባመኑ ከዚያ (ከተከለከሉት ነገሮች ሁሉ) ከተጠነቀቁና ስራን ካሳመሩ ከመከልከሉ በፊት በተመገቡት ነገር ኃጢአት የለባቸውም።* አላህ በጎ ሰሪዎችን ሁሉ ይወዳልና።

* አነስ ቢን ማሊክ ባስተላለፉት ዘገባ እንዲህ ብለዋል።«አስካሪ መጠጥ የተከለከለ መሆኑን የሚደነግገው የቁርአን አንቀፅ ሲወርድ በአቡጠልሐ ቤት ሰዎችን እያስተናገድኩኝ ነበር። ከዚያ አስካሪ መጠጥ ተከለከለ የሚል ህግ ወርዷል የሚል ድምፅ ሲሰማ ወዲያውኑ መጠጡ በየመንገዱ ተደፋ። አቡጠልሀም አውጣና መጠጡን ድፋው አለኝ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች የሞቱ ሰዎችን ሲያነሱ ብዙዎቹ መጠጥ በሆዳቸው እያለ ነው የሞቱት ከድንጋጌው መውጣት በፊት የሞቱ ሰዎችን ሁኔታ በተመለከተ ትካዜና ሀዘን መግባታቻውን ቀጠሉ ከዚያም ይህ አንቀፅ ወረደ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَيَبۡلُوَنَّكُمُ ٱللَّهُ بِشَيۡءٖ مِّنَ ٱلصَّيۡدِ تَنَالُهُۥٓ أَيۡدِيكُمۡ وَرِمَاحُكُمۡ
لِيَعۡلَمَ ٱللَّهُ مَن يَخَافُهُۥ بِٱلۡغَيۡبِۚ فَمَنِ ٱعۡتَدَىٰ بَعۡدَ ذَٰلِكَ فَلَهُۥ عَذَابٌ أَلِيمٞ ٩٤ يَٰٓأَيُّهَا
ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَقۡتُلُواْ ٱلصَّيۡدَ وَأَنتُمۡ حُرُمٞۚ وَمَن قَتَلَهُۥ مِنكُم مُّتَعَمِّدٗا فَجَزَآءٞ مِّثۡلُ مَا
قَتَلَ مِنَ ٱلنَّعَمِ يَحۡكُمُ بِهِۦ ذَوَا عَدۡلٖ مِّنكُمۡ هَدۡيَۢا بَٰلِغَ ٱلۡكَعۡبَةِ أَوۡ كَفَّٰرَةٞ طَعَامُ مَسَٰكِينَ

أَوۡ عَدۡلُ ذَٰلِكَ صِيَامٗا لِّيَذُوقَ وَبَالَ أَمۡرِهِۦۗ عَفَا ٱللَّهُ عَمَّا سَلَفَۚ وَمَنۡ عَادَ فَيَنتَقِمُ ٱللَّهُ
مِنۡهُۚ وَٱللَّهُ عَزِيزٞ ذُو ٱنتِقَامٍ ٩٥ أُحِلَّ لَكُمۡ صَيۡدُ ٱلۡبَحۡرِ وَطَعَامُهُۥ مَتَٰعٗا لَّكُمۡ وَلِلسَّيَّارَةِۖ
وَحُرِّمَ عَلَيۡكُمۡ صَيۡدُ ٱلۡبَرِّ مَا دُمۡتُمۡ حُرُمٗاۗ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِيٓ إِلَيۡهِ تُحۡشَرُونَ ٩٦

**94-96.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህ በሐጅ ጊዜ እጆቻችሁና ጦሮቻችሁ በሚያገኙት በሚያድኑት ታዳኝ አውሬ አላህን በሩቁ ሆኖ የሚፈራውን ሰው ሊገልፅ ይሞክራችኋል። ከዚያ በኋላ ወሰንን ያለፈና ያደነ ሰው ሁሉ አሳማሚ ቅጣት አለበት። እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ እናንተ በሐጅ ስራ ውስጥ ስትሆኑ አውሬን አትግደሉ። ከናንተም እያወቀ አውሬን የገደለ ሰው ቅጣቱ ከናንተ መካከል ሁለት ፍትሀዊነት ባለቤቶች የሚፈርዱበትና ወደ ካዕባ ደራሽ መስዋዕት ሲሆን ከቤት እንሰሳዎች የገደለውን ነገር ብጤ መስጠት ወይም ሚስኪኖችን ማብላት ወይም የዚህን ልክ መፆም ማሰረዣው ነው። ይህም የስራውን ከባድ ቅጣት እንዲቀምስ ነው። ሳይከለከል በፊት ካለፈው ነገር አላህ ይቅርታ አደረገ። ወደ ጥፋቱ የተመለሰን ሰው ሁሉ አላህ ይቀበለዋል። አላህ አሸናፊና ፀፀትን የመቀበል ባለቤት ነው። (ሙስሊሞች ሆይ)፣ የባህር እንሰሳና ምግቡ ለእናንተና ለመንገደኞች ሁሉ መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ ተፈቀደላችሁ። በሐጅ ላይ እስካላችሁ ድረስ ግን የየብስ አውሬ በእናንተ ላይ እርም ተደረገ። ያንን ወደ እርሱ የምትሰበሰቡበትን አላህን ፍሩ።

۞ جَعَلَ ٱللَّهُ ٱلۡكَعۡبَةَ ٱلۡبَيۡتَ ٱلۡحَرَامَ قِيَٰمٗا لِّلنَّاسِ وَٱلشَّهۡرَ ٱلۡحَرَامَ وَٱلۡهَدۡيَ وَٱلۡقَلَٰٓئِدَۚ ذَٰلِكَ
لِتَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَأَنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ ٩٧
ٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ وَأَنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٩٨

**97-98.** አላህ ያ! የተከበረውን ቤት ካዕባን፤ ክልክል የሆነውንም ወር፤ (ወደ መካ የሚወሰደውን) መስዋዕቱንና ባለ ምልክቶቹን መንጋዎች ለሰዎች የእምነት ዋልታ መቋቋሚያ አደረገ። ይህ የሆነው አላህ በሰማያትና በምድር ያለውን ሁሉ ጠንቅቆ የሚያውቅ መሆኑንና ሁሉን ነገር አዋቂ መሆኑን እንድታውቁ ዘንድ ነው። (ሰዎች ሆይ)፣ አላህ ቅጣተ ብርቱ መሀሪና አዛኝ መሆኑን እወቁ።

مَّا عَلَى ٱلرَّسُولِ إِلَّا ٱلْبَلَٰغُ ۗ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ مَا تُبْدُونَ وَمَا تَكْتُمُونَ ﴿٩٩﴾ قُل لَّا يَسْتَوِى ٱلْخَبِيثُ
وَٱلطَّيِّبُ وَلَوْ أَعْجَبَكَ كَثْرَةُ ٱلْخَبِيثِ ۚ فَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ يَٰٓأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿١٠٠﴾

**99-100.** በመልዕክተኛው ላይ በትክክል መልዕክቱን ማድረስ እንጂ ሌላ የለበትም። አላህ የምትገልጹትን ነገርም ሆነ የምትደብቁትን ሁሉ ያውቃል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመጥፎው ነገር ብዛት ቢያስገርምህም እንኳ መጥፎና ጥሩ መቸም አይስተካከሉም። ባለ ልቦች ሆይ፣ ከእሳት ትድኑ ዘንድ አላህን ብቻ ፍሩ በላቸው።

ከመዐዱ ምዕራፍ ከ (90-100) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ኸምርን በተመለከተ ለመጨረሻ ጊዜ የወረደ ነው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ) አነስ ቢን ማሊክ ባስተላለፉት ዘገባ እንዲህ ይላሉ«ኸምር» (አስካሪ መጠጥ) የተከለከለ መሆኑን የሚደነገግው የቁርኣን አንቀፅ ሲወርድ በአቡጦልሀ ቤት ሰዎችን እያስተናገድኩኝ ነበር ከዚያም አስካሪ መጠጥ የተከለከለ የሚል ህግ ወርዷል የሚል ድምፅ ሲሰማ ወዲያውኑ መጠጡን በየመንገዱ ተደፉ አቡጦልሀም አውጣና መጠጡን ድፋው አለኝ በዚህ ጊዜ አንዳንድ ሰዎች የሞቱ ሰዎችን እያነሱ ብዙዎቹ ኸምር በሆዳቸው እያለ ነው የሞቱት በማለት ከድንጋጌው መውጣት በፊት የሞቱ ሰዎችን ሁኔታ በተመለከተ ትካዜና ሀዘን ውስጥ መግባታቸውን ቀጠሉ ከዚያም ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ፤ ሲዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَسْـَٔلُوا۟ عَنْ أَشْيَآءَ إِن تُبْدَ لَكُمْ تَسُؤْكُمْ وَإِن تَسْـَٔلُوا۟ عَنْهَا حِينَ
يُنَزَّلُ ٱلْقُرْءَانُ تُبْدَ لَكُمْ عَفَا ٱللَّهُ عَنْهَا ۗ وَٱللَّهُ غَفُورٌ حَلِيمٌ ﴿١٠١﴾ قَدْ سَأَلَهَا قَوْمٌ مِّن
قَبْلِكُمْ ثُمَّ أَصْبَحُوا۟ بِهَا كَٰفِرِينَ ﴿١٠٢﴾

**101-102.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ለእናንተ ቢገለፁ ከሚያስከፏችሁ ነገሮች አትጠይቁ። ቁርኣንም በሚወርድበት ጊዜ ከእርሷ ብትጠይቁ ለእናንተ ትገለፃለች። ከእርሷ ግን አላህ ይቅርታ አደረገ። አላህ መሀሪና ታጋሽ ነውና። ከናንተ በፊት የነበሩ የተወሰኑ ሕዝቦች ጠየቁ ከዚያ በእርሱ ምክንያት ከካሐዲያን ሆኑ።

ከመዐዱ ምዕራፍ (101) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-አንዳንድ ግለሰቦች ነብዩን (ﷺ) ለማብሸቅ በማሰብ የሆነ ያልሆነ ጥያቄዎችን እየደረደሩ ያሰለቿቸው ነበር ለምሳሌ አባቴ ማን ነው? ግመሌ የት ናት? የሚሉ አላስፈላጊ ጥያቄዎች ይገኙባቸዋል። በዚህ ጊዜ ነበር አላህ ይህን አንቀፅ በማውረድ ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በመደርደር መልዕክተኛውን ማስቸገር ተገቢ እንዳልሆነ ደነገገ። (ቡኻሪ፤ ዋሒዲ፤ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)

مَا جَعَلَ ٱللَّهُ مِنۢ بَحِيرَةٖ وَلَا سَآئِبَةٖ وَلَا وَصِيلَةٖ وَلَا حَامٖ وَلَٰكِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يَفۡتَرُونَ عَلَى
ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَۖ وَأَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ ١٠٣ وَإِذَا قِيلَ لَهُمۡ تَعَالَوۡاْ إِلَىٰ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ وَإِلَى ٱلرَّسُولِ
قَالُواْ حَسۡبُنَا مَا وَجَدۡنَا عَلَيۡهِ ءَابَآءَنَآۚ أَوَلَوۡ كَانَ ءَابَآؤُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ شَيۡـٔٗا وَلَا يَهۡتَدُونَ ١٠٤

**103-104.** አላህ በሒራ፣ ሳኢባም፣ ወሲላና ሀምን* የተባሉ ነገሮች ከሸሪዓ አላደረገም። ግን እነዚያ በአላህ የካዱ ህዝቦች በአላህ ላይ ውሸትን ይቀጥፋሉ። አብዛሀኞቻቸው ትክክለኛውን አካል አያውቁም። ለነርሱም አላህ ወደ አወረደውና ወደ መልዕክተኛው ኑ በተባሉ ጊዜ አባቶቻችንን በርሱ ላይ ያገኘንበት መንገድ ይበቃናል ይላሉ። አባቶቻቸው ምንም የማያውቁና ወደ ቀናው መንገድ የማይመሩ ቢሆኑም (ይህ ማለት ይበቃቸዋልን?)

* በሒራ፡- በተከታታይ አስር የወለደችን ግመል ጆሮዋን ቀደው ማንም እንዳይጠቀምባት ይለቋት የነበረች ግመል ናት።

ሳኢባ፡- ከመንገድ በሰላም ሲመለስ ወይም ከበሺታ ሲድን ነፃ ይለቋት የነበረች ግመል ናት።

ወሲላ፡- ወንድና ሴት በአንድ ጊዜ በመንትያ የወለደች ግመል እንዳትታረድ ነፃ ይለቋት ነበር።

ሃም፡- አስር ያስወለደ ወንድ ግመል እንዳይጋልብ ነፃ ይለቁት ነበር።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ عَلَيۡكُمۡ أَنفُسَكُمۡۖ لَا يَضُرُّكُم مَّن ضَلَّ إِذَا ٱهۡتَدَيۡتُمۡۚ إِلَى ٱللَّهِ
مَرۡجِعُكُمۡ جَمِيعٗا فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ١٠٥

**105.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ነፍሶቻችሁን ከእሳት ጠብቁ። ራሳችሁን ወደቀናው መንገድ ከመራችሁ የሌሎች መሳሳት አይጎዳችሁም። የሁላችሁም መመለሻ ወደ አላህ ብቻ ነው። እናም ትሰሩት የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል።

ከመዐዱ ምዕራፍ (105) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-ነብዩ የሀጀርን ሰዎች እንዲያስተምር ከእሱሃቦቻቸው መካከል አንዱን ላኩት። እሱም በትዕዛዙ መሰረት እነሱ ዘንድ ደርሶ አረቦች፤ ይሁዶች፤ ክርስቲያኖች፤ ሳቢያኖች እና መጁሶች በነበሩበት ይህን መልዕክት አስተላለፈ። «ኢስላምን እምቢ ካሉህ ሰይፍ እንጂ ሌላ እንዳትቀበላቸው። የመፅሐፍ ሰዎችን እና መጁሶችን ግብርም ቢሆን ተቀበላቸው ብለውት ስለነበር እሱም ይህን ደብዳቤ አነበበላቸው። አረቦች ኢስላምን ሲቀበሉ የመፅሐፍ ሰዎችና መጁሶች ግብርን መክፈል ጀመሩ በዚህ ጊዜ ነበር አስመሳይ አረቦች «የሙሐመድ ነገር ይገርማል። አላህ የላከኝ ሰዎችን እስከሚሰልሙ ድረስ እንድንዋጋ ነው። ግብር የምንቀበለው ከመፅሐፍ ባለቤቶች ብቻ ነው ሲል ኖሮ እነሆ ከአጋሪዎች (ጣኦት አምላኪዎች) ግብርን መቀበል ጀመረ። እያሉ በማስወራታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ እና ኢብኑ ከሲር)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ شَهَٰدَةُ بَيۡنِكُمۡ إِذَا حَضَرَ أَحَدَكُمُ ٱلۡمَوۡتُ حِينَ ٱلۡوَصِيَّةِ ٱثۡنَانِ ذَوَا
عَدۡلٖ مِّنكُمۡ أَوۡ ءَاخَرَانِ مِنۡ غَيۡرِكُمۡ إِنۡ أَنتُمۡ ضَرَبۡتُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَأَصَٰبَتۡكُم مُّصِيبَةُ ٱلۡمَوۡتِۚ
تَحۡبِسُونَهُمَا مِنۢ بَعۡدِ ٱلصَّلَوٰةِ فَيُقۡسِمَانِ بِٱللَّهِ إِنِ ٱرۡتَبۡتُمۡ لَا نَشۡتَرِي بِهِۦ ثَمَنٗا وَلَوۡ كَانَ ذَا قُرۡبَىٰ
وَلَا نَكۡتُمُ شَهَٰدَةَ ٱللَّهِ إِنَّآ إِذٗا لَّمِنَ ٱلۡأٓثِمِينَ ١٠٦ فَإِنۡ عُثِرَ عَلَىٰٓ أَنَّهُمَا ٱسۡتَحَقَّآ إِثۡمٗا فَـَٔاخَرَانِ
يَقُومَانِ مَقَامَهُمَا مِنَ ٱلَّذِينَ ٱسۡتَحَقَّ عَلَيۡهِمُ ٱلۡأَوۡلَيَٰنِ فَيُقۡسِمَانِ بِٱللَّهِ لَشَهَٰدَتُنَآ أَحَقُّ مِن
شَهَٰدَتِهِمَا وَمَا ٱعۡتَدَيۡنَآ إِنَّآ إِذٗا لَّمِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٠٧ ذَٰلِكَ أَدۡنَىٰٓ أَن يَأۡتُواْ بِٱلشَّهَٰدَةِ عَلَىٰ وَجۡهِهَآ
أَوۡ يَخَافُوٓاْ أَن تُرَدَّ أَيۡمَٰنُۢ بَعۡدَ أَيۡمَٰنِهِمۡۗ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَٱسۡمَعُواْۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ١٠٨

**106-108.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አንዳችሁን ሞት በመጣበት ጊዜ በኑዛዜ ወቅት በመካከላችሁ ከናንተ መካከል ሁለት የትክክለኛነት ባለቤቶች የሆኑ ሰዎች ምስክሮችን ያስመስክር ወይም በምድር ብትጓዙና የሞት አደጋ ብትነካችሁ ከሌሎቻችሁ (እምነት ተከታዮች) የሆኑ ሁለት ሌሎች ሰዎች (መመስከር) ነው። ብትጠራጠሩ ከአሱር ሶላት በኋላ አቁሟቸውና (የሚመሰክርለት ሰው) የዝምድና ባለቤት ቢሆንም እንኳን በእርሱ ዋጋን አንገዛም። የአላህን ምስክርነት አንደብቅም። ያን ጊዜማ ደብቀን ብንገኝ ከኃጢአተኞች ነን ብለው በአላህ ስም ይምላሉ። ሆኖም እነርሱ ኃጢአት (በውሸት መስክረው) የተገቡ መሆናቸው ቢታወቅ ከእነዚያ ከሟቹ ቅርብ ዘመዶች በመሆን ውርስ ከተገባቸው የሆኑ ሁለት ሌሎች ሰዎች በስፍራቸው በምስክሮች ስፍራ ይቆሙና ምስክርነታችን ከእነርሱ ምስክርነት ይልቅ እውነት ነው ወሰንም አላለፍንም። ያን ጊዜ ከበዳዩቹ ነን ሲሉ በአላህ ይምላሉ። ይህ (አሰራር) ምስክርነት በተገቢው ላይ ለማምጣታቸው ወይም ከመሀላዎቻቸው በኋላ የመሀላዎችን ወደ ወራሾች መመለስን ለመፍራት በጣም የቀረበ መንገድ ነው። አላህን ብቻ ፍሩ። እሱን ብቻ ስሙትም። አላህ አመፀኛ ሕዝቦችን ሁሉ ወደ ትክክለኛው አይመራምና።

ከመዐዱ ምዕራፍ ከ (97-108) ኛው አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ተሚም አዳሪንና አዲይ ቢን ዘይድን ወደ መካ ይመለሱ ነበር። አንድ ቀን ከበኒ ሰህም ጎሳ የሆነ አንድ ወጣት አብሯቸው ወደ መካ ለመጓዝ መንገድ ላይ ማንም ሙስሊም ከሌለበት ስፍራ ላይ ህመም ፀናበትና ለመሞት ሲያጣጥር ንብረቱን ለቤተሰቡ እንዲሰጡለት አደራ አላቸው። ከወጣቱ ህልፈት በኋላ አደራ የተጣለባቸው ሰዎች ንብረቱን ለቤተሰቡ ሲሰጡ አንድ የብር ዕቃ አስቀሩና ሌላውን አስረከበው ወደ ነብዩ መጡ። «አንድም ነገር አላስቀራችሁምን? ሁሉንም ነገር አስረከባችኋልን» አሏቸው ሰዎቹ ያስቀሩት የብር ዕቃ በመካ ከተማ በአንድ ግለሰብ እጅ ተገኘ። እርሱም ከተሚምና ከአዲይ የገዛቸው መሆኑን አጋለጠ። ከዚያም በኋላ የልጁ ወገኖች የሆኑ ሁለት ሰዎች መጥተው «ይህማ የልጃችን ንብረት ለመሆኑ እንምላለን» ብለው በመማላቸው እቃውን ወሰዱ። በዚህ ጊዜ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ቡኻሪ እና ሱዩጢ)

**ከመዐዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (82-108) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አንዳንድ ግለሰቦች ነብዩን ለማብሸቅ የሆነ ያልሆነ ጥያቄዎችን እየደረደሩ ያሰለቿቸው ነበር ለምሳሌ አባቴ ማንነው (ግመሌ የትናት) የሚሉና መሰል አላስፈላጊ ጥያቄዎችን ማቅረብ ይገኙበታል። በዚህ ጊዜ ነበር አላህ ይህንን አንቀፅ በማውረድ ተገቢ ያልሆኑ ጥያቄዎችን በመደርደር መልክተኛውን ማስቸገር ተገቢ እንዳልሆነ ደነገገ።
2. ተሚም ደረይና ዳዒይ ቢን በዳእ ወደ መካ ይመላለሱ ነበር አንድ ቀን ከበኒ ሰህም ጎሣ የሆነ አንድ ወጣት አብሯቸው ወደ መካ ሲጓዝ መንገድ ላይ ማንም ሙስሊም በሌለበት ቦታ ላይ ህመም ፀናበትና ለመሞት ሲያጣጥር ንብረቱን እንዲሰጥለት አደራ አላቸውና ሌላውን አስረክባችኋልን አሏቸው ነገር ግን ያስቀሩት የብር ዕቃ በመካ ከተማ በአንድ ግለሰብ እጅ ተገኘ እርሱም ከተሚማና ከሰኢዳይ የገዛቸው መሆኑን አጋለጠ ከዚያ በኋላ የልጁ ወገኖች የሆኑ ሁለት ሰዎች መጥተው ይህማ የልጃችን ንብረት ለመሆኑ እንምላለን ብለው በመማላቸው እቃውን ወሰዱ። በዚህ ጊዜ የሱረቱል ማኢዳህ ቁጥር ከ (97-108) ያሉት አናቅፅ ወረዱ።

۞ يَوْمَ يَجْمَعُ ٱللَّهُ ٱلرُّسُلَ فَيَقُولُ مَاذَآ أُجِبْتُمْ ۖ قَالُواْ لَا عِلْمَ لَنَآ ۖ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّٰمُ ٱلْغُيُوبِ ﴿١٠٩﴾

**109.** (ሰዎች ሆይ!) አላህ መልክተኞቹን ሁሉ ሰብስቦ ሕዝቦች ምን መለሱላችሁ? በሚልበት ጊዜ (የሚሆነውን አስታውሱ)፡- ሕዝቦቻችሁ ምን መለሱላችሁ (ነብያት) ‹እኛ እውቀቱ የለንም። ሩቅ ሚስጥሮችን ሁሉ ጠንቅቀህ የምታውቀው አንተው ነህ› ይላሉ።

إِذْ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبْنَ مَرْيَمَ ٱذْكُرْ نِعْمَتِى عَلَيْكَ وَعَلَىٰ وَٰلِدَتِكَ إِذْ أَيَّدتُّكَ بِرُوحِ ٱلْقُدُسِ تُكَلِّمُ ٱلنَّاسَ فِى ٱلْمَهْدِ وَكَهْلًا ۖ وَإِذْ عَلَّمْتُكَ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحِكْمَةَ وَٱلتَّوْرَىٰةَ وَٱلْإِنجِيلَ ۖ وَإِذْ تَخْلُقُ مِنَ ٱلطِّينِ كَهَيْـَٔةِ ٱلطَّيْرِ بِإِذْنِى فَتَنفُخُ فِيهَا فَتَكُونُ طَيْرًۢا بِإِذْنِى ۖ وَتُبْرِئُ ٱلْأَكْمَهَ وَٱلْأَبْرَصَ بِإِذْنِى ۖ وَإِذْ تُخْرِجُ ٱلْمَوْتَىٰ بِإِذْنِى ۖ وَإِذْ كَفَفْتُ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ عَنكَ إِذْ جِئْتَهُم بِٱلْبَيِّنَٰتِ فَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنْهُمْ إِنْ هَٰذَآ إِلَّا سِحْرٌ مُّبِينٌ ﴿١١٠﴾ وَإِذْ أَوْحَيْتُ إِلَى ٱلْحَوَارِيِّـۧنَ أَنْ ءَامِنُواْ بِى وَبِرَسُولِى قَالُوٓاْ ءَامَنَّا وَٱشْهَدْ بِأَنَّنَا مُسْلِمُونَ ﴿١١١﴾

**110-111.** መልዕክተኛችን አላህ እንዲህ በሚልበት ጊዜ የሚሆነውን አስታውስ፡- ‹የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ፣ ለአንተና ለእናትህ የዋልኩላችሁን ውለታ አስታውስ። በመንፈስ ቅዱስም በጅብሪል አጠናከርኩህ። በሕጻንነትህም አድገህም ሰዎችን ማናገር ቻልክ። በመላኩ ጅብሪል መጽሐፉንና ጥበብን ተውራትንና ኢንጂልንም አስተማርኩህ። ከጭቃም የወፍ ቅርጽ ዓይነት መሥራት ቻልክ። ነፍስንም በፈቃዴ በሞቱት ላይ ዘራህበት። በፈቃዴም

እውነተኛ በራሪ ሆነ። እውር ሆኖ የተወለደንና ለምጻምን በፈቃዴ መፈወስ ቻልክ። ሟችንም በፈቃዴ አስነሳህ። የኢስራኢልንም ልጆች ግልጽ መረጃ ባመጣህላቸው ጊዜ ሊያጠቁህ ሲያስቡ አቀብኩልህ። ከመካከላቸውም እነዚያ በአላህ የካዱት ይህ ግልጽ ድግምት ነው ባሉ ጊዜ። (ይህን ሁሉ ውለታዬን አስታውስ)። ለሃዋሪያትም፡- ‹በእኔና በመልዕክተኛዬ እመኑ።› የሚል ራዕይ በገለጽኩ ጊዜም (የሆነውን አስታውስ)። ‹አምነናል። እኛ ሙስሊሞች ለመሆናችን ምስክር ሁን› አሉም።

إِذۡ قَالَ ٱلۡحَوَارِيُّونَ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ هَلۡ يَسۡتَطِيعُ رَبُّكَ أَن يُنَزِّلَ عَلَيۡنَا مَآئِدَةٗ مِّنَ
ٱلسَّمَآءِۖ قَالَ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ﴿١١٢﴾ قَالُواْ نُرِيدُ أَن نَّأۡكُلَ مِنۡهَا وَتَطۡمَئِنَّ
قُلُوبُنَا وَنَعۡلَمَ أَن قَدۡ صَدَقۡتَنَا وَنَكُونَ عَلَيۡهَا مِنَ ٱلشَّٰهِدِينَ ﴿١١٣﴾ قَالَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ
ٱللَّهُمَّ رَبَّنَآ أَنزِلۡ عَلَيۡنَا مَآئِدَةٗ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ تَكُونُ لَنَا عِيدٗا لِّأَوَّلِنَا وَءَاخِرِنَا وَءَايَةٗ مِّنكَۖ
وَٱرۡزُقۡنَا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ﴿١١٤﴾ قَالَ ٱللَّهُ إِنِّي مُنَزِّلُهَا عَلَيۡكُمۡۖ فَمَن يَكۡفُرۡ بَعۡدُ مِنكُمۡ
فَإِنِّيٓ أُعَذِّبُهُۥ عَذَابٗا لَّآ أُعَذِّبُهُۥٓ أَحَدٗا مِّنَ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١١٥﴾

**112-115.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፣ ሃዋሪያቶችም፡- ‹የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ፣ ጌታህ ከሰማይ ማዕድ ሊያወርድልን ይቻላልን› ባሉ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ዒሳም፡- ‹ትክክለኛ አማኞች ከሆናችሁ አላህን ብቻ ፍሩ› አለ። ‹ከእርሷ ልንመገብ ልቦቻችንም እርካታን ይጎናፀፉ ዘንድ ብቻ ነው ይህን የጠየቅነው። እውነቱን እንደ ነገርከን በተጨባጭ ልናውቅና ለዚህም መስካሪዎች እንሆናለን› አሉ። የመርየም ልጅ ዒሳም፡- ‹ጌታችን አላህ ሆይ፣ ለእኛ ለመጀመሪያዎቻችንና መጭዎቹም ትውልዶች በዓል (የደስታ እለት) ከአንተ የሆነችም ተዐምር ትሆንልን ዘንድ ከሰማይ ማዕድን አውርድልን። ሲሳይንም ለግሰን። አንተ ወደር የሌለህ ለጋሽ ነህና› አለ። አላህ፡- ማዕዷን አወርድላችኋለሁ። ግና ከዚህ ተአምር በኋላ ከውስጣችሁ በእኔ የካዱ ሰዎች ሁሉ በዓለማት ላይ ማንንም የማልቀጣውን አስከፊ ቅጣት እቀጣቸዋለሁ አለ።

وَإِذۡ قَالَ ٱللَّهُ يَٰعِيسَى ٱبۡنَ مَرۡيَمَ ءَأَنتَ قُلۡتَ لِلنَّاسِ ٱتَّخِذُونِي وَأُمِّيَ إِلَٰهَيۡنِ مِن دُونِ ٱللَّهِۖ
قَالَ سُبۡحَٰنَكَ مَا يَكُونُ لِيٓ أَنۡ أَقُولَ مَا لَيۡسَ لِي بِحَقٍّۚ إِن كُنتُ قُلۡتُهُۥ فَقَدۡ عَلِمۡتَهُۥۚ تَعۡلَمُ
مَا فِي نَفۡسِي وَلَآ أَعۡلَمُ مَا فِي نَفۡسِكَۚ إِنَّكَ أَنتَ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ ﴿١١٦﴾ مَا قُلۡتُ لَهُمۡ

إِلَّا مَآ أَمَرۡتَنِي بِهِۦٓ أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبَّكُمۡۚ وَكُنتُ عَلَيۡهِمۡ شَهِيدٗا مَّا دُمۡتُ فِيهِمۡۖ
فَلَمَّا تَوَفَّيۡتَنِي كُنتَ أَنتَ ٱلرَّقِيبَ عَلَيۡهِمۡۚ وَأَنتَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ١١٧ إِن تُعَذِّبۡهُمۡ فَإِنَّهُمۡ
عِبَادُكَۖ وَإِن تَغۡفِرۡ لَهُمۡ فَإِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ١١٨

**116-118.** (መልዕክተኛች ሙሐመድ ሆይ!) አላህ፦ ‹የመርየም ልጅ ዒሳ ሆይ፣ ሰዎችን እኔንና እናቴን ከአላህ ውጭ ሁለት አማልዕክት አድርጋችሁ ያዙን ብለሃልን» በሚለው ጊዜ (የሚሆነውን አስታውስ)። ዒሳም፦ ‹ክብርና ልዕልና ለአንተ ብቻ ይሁን! ለእኔ ልለው የማይገባኝን ነገር ማለቴ ፈጽሞ አግባብ አይደለም። ይህን ተናግሬ ከሆነም ታውቀዋለህ። አንተ በውስጤ ያለውን ሁሉ ጠንቅቀህ ታውቃለህ። እኔ ግን በአንተ ውስጥ ያለውን አላውቅም። አንተ ሩቅ ሚስጥራትን ሁሉ ዐዋቂ ነህና። የነገርኳቸው ያን ያዘዝከኝን ብቻ ነው። የእኔም የእናንተም ጌታ የሆነውን አላህን ብቻ አምልኩ ነው ያልኳቸው። በመካከላቸው በነበርኩበት ወቅት ስለ እነርሱ መስካሪ ነበርኩ። እንዳርግ ካደረግከኝ በኋላ ግን የእነርሱ ጠባቂና ተቆጣጣሪ አንተው ብቻ ነበርክ። አንተ በሁሉም ነገር ላይ መስካሪ ነህና ይላልም። ብትቀጣቸው እነርሱ የአንተው ባሮችህ ናቸው። ብትምራቸው ደግሞ አንተ ኃያልና ጥበበኛ* ነህ (ይላልም)።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «በእርግጥ እናንተ በትንሳኤ ቀን በአንድ ላይ ትሰበሳባላችሁ። ወደ ግራ አቅጣጫ ወደ እሳት የሚገፈተሩ ሰዎች አሉ። እኔም መልካሙ የአላህ ባሪያ ዒሳ እንዳለው «በውስጣቸው እስካለሁ ድረስ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርኩ፤ ባስነሳኸኝም ጊዜ አንተ በነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነበርክ፤ አንተም በነገሩ ሁሉ ላይ አዋቂ ነህ። ብትቀጣቸው እነርሱ ባሮችህ ናቸው። ለነርሱ ብትምርም አንተ አሸናፊው ጥበበኛው ነህ፤ እላለሁ» ብለዋል።
አቡ ዘር እንደሚሉት ደግሞ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) «ይህን አንቀፅ አንድ ሌሊት ሙሉ ሲደጋግሙት አደሩ»ብለዋል።

قَالَ ٱللَّهُ هَٰذَا يَوۡمُ يَنفَعُ ٱلصَّٰدِقِينَ صِدۡقُهُمۡۚ لَهُمۡ جَنَّٰتٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ
فِيهَآ أَبَدٗاۖ رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ١١٩ لِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا فِيهِنَّۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرُۢ ١٢٠

**119-120.** አላህም እንዲህ ይላል፦ ይህ ቀን እውነት ለእውነተኞች የሚጠቅምበት ቀን ነው። ለእውነተኞች ከስሮቿ ወንዞች የሚፈሱባት ገነት ተዘጋጅቶላቸዋል። በውስጧም ለዘንተ ዓለም ይኖራሉ። አላህ በእነርሱ ተግባር ተደስቷል። እነርሱም በእርሱ ችሮታ ተደስተዋል። ይህ ታላቅ ስኬት ነውና። የሰማያት የምድርና በውስጣቸው ያሉ ፍጡራን ሁሉ ባለቤትነት የአላህ ብቻ ነው። እርሱ በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነውና።

**ከመዐዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (109-120) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሁሉም ነብያት የቂያማ ዕለት በህዝቦቻቻው ላይ የምስክርነት ቃል እንደሚሰጡ፤
2. የሰው ልጆች ከአላህ ጋር ሊኖራቸው የሚገቡ ስርዓቶች፤
3. በነብዩ ዒሳና በእናታቸው በመርየም ላይ አላህ የዋለላቸውን ፀጋ ማስታወስ፡፡
4. አላህ ነብዩ ዒሳ ያጠናከረባቸው ልዩ ልዩ ተዐምራቶቻቸው ለምሳሌ ያለአባት መወለዳቸው፤ ገና ጡት በሚጠቡበት እድሜያቸው ሰዎችን ከማናገር አልፈው ወደ አላህ አንድነት ጥሪ ማድረጋቸው፤
5. የአላህን ችሎታና ምሉዕነት፤ አላህ የነብያትንና የሷሊሆችን ዱዓ እንደሚቀበላቸው፤
6. «ማዕድ» መውረዱ የነብዩ ዒሳን ነብይነት ከሚያረጋግጡ እውነቶች አንዱ እንደሆኑ፤
7. አላህ በጥፋታቸው ባሮቹን መቅጣቱ ፍትህ እንደሆነ፤
8. ትክክለኛ እምነትና እውነት መናገር በቂያማ ቀን ያላቸው ጠቀሜታ ወደር የለሽ መሆኑን እንማራለን፡፡

## በአላህ ፈቃድ የመዐዱ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ፡፡

# ምዕራፍ (6)
# የቤት እንስሳት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልአንዓም)

سُورَةُ الأَنعَامِ

## የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (165) መቶ ስልሳ አምስት ናቸው።

## የሱረቱ አል አንዓም መግቢያ

በአንድ ጊዜ እንደ ወረደና በነብዩ ፀሀፊዎችን አዘው እንደተፃፈች ኢብኑ ዐባስ ተናግረዋል።

ከአንቀፅ (2) ከሰፈረው መልዕክት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ብዙ ቁርኣናዊ አናቅፅ ያሉ ሊሆን ከእነዚህም መካከል በአልፉርቃን (54) ኛው አንቀፅ፤ አርሩም (20) ኛው አንቀፅ፤ አል-ሑጁራት (13) ኛው አንቀፅ፤ በዋነኛነት የሚጠቀሱ ናቸው። ሁሉም ተመሳሳይ መልዕክት አላቸው። ሰዎች ሁሉ አንድ አይነት መሆናቸውን፤ መነሻቸው አደም፤ መጨረሻቸው ሞት መሆኑን፤ በሁለቱ መካከልም ልፋት እና ድካም ያለ መሆኑን ያብራራሉ። ከዚህ ላይ መነሳት ካለባቸው የቀደምት ሙስሊሞች አባባሎች መካከል የሚከተሉትን በጥቂቱ እንመልከት፡-

1. ዐሊይ ቢን አቢጧሊብ «ኩራት ለሰው ልጅ ምኑ ነው መነሻው ጠብታ፤ መጨረሻው ግም በመሀከሉም ቆሻሻ ተሸካሚ ሆኖ፤» ብለዋል።
2. ኢትዮጵያዊው ቢላል «አባትህ ማነው» ተብለው በተጠየቁ ጊዜ ያለምንም ማመንታት «እኔ የዚያ አላህ መላኢኮችን ያሰገደለት (የአደም) ልጅ ነኝ» ብለዋል።
3. ሰልማን አልፋሪሲም «ሰዎች በየዘሮቻቸው ሲፎካከሩ የእኔ አባት ግን ኢስላም ነው» ያሉት ይጠቀሳሉ። በሰማይም ሆነ በምድር የሚመለክ ማለት ነው። ምክንያቱም አላህ የሚለው ቃል እብኑ ከሲርና ጦበሪ እንደሚሉት «ማምለክ» ከሚለው ስርወ ቃል የተመሰረተ ነውና ብለዋል። ሲወርድ በአንድ ጊዜ ከመሆኑም በተጨማሪ ሰባ ሺህ መላኢካ በዕልልታ እዳጀበው ተዘግቧል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَجَعَلَ ٱلظُّلُمَٰتِ وَٱلنُّورَۖ ثُمَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِرَبِّهِمۡ
يَعۡدِلُونَ ١ هُوَ ٱلَّذِي خَلَقَكُم مِّن طِينٖ ثُمَّ قَضَىٰٓ أَجَلٗاۖ وَأَجَلٞ مُّسَمًّى عِندَهُۥۖ ثُمَّ أَنتُمۡ
تَمۡتَرُونَ ٢ وَهُوَ ٱللَّهُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَفِي ٱلۡأَرۡضِ يَعۡلَمُ سِرَّكُمۡ وَجَهۡرَكُمۡ وَيَعۡلَمُ مَا تَكۡسِبُونَ ٣

**1-3.** ምስጋና ሁሉ ለዚያ ሰማያትንና ምድርን ለፈጠረ ጨለማዎችንና ብርሃንን ላደረገ ለአላህ የተገባ ነው። ከዚያ እነዚያ በእርሱ የካዱ ሰዎች ሁሉ ጣዖታትን ከጌታቸው ጋር ያስተካክላሉ። እርሱ ያ ከጭቃ የፈጠራችሁ ከዚያም የሞት ጊዜ የወሰነ ነው። እርሱም ዘንድ ለትንሳኤ የተወሰነ ጊዜ አለ። ከዚያም እናንተ በመቀስቀሳችሁ ትጠራጠራላችሁ። እርሱ ያ በሰማያትና በምድር ሊገዙት የሚገባው አላህ ብቻ ነው። ሚስጥራችሁንም ሆነ ግልፃችሁን ጠንቅቆ ያውቃል። (ሰዎች ሆይ፦) የምትሰሩትን ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል።

وَمَا تَأۡتِيهِم مِّنۡ ءَايَةٖ مِّنۡ ءَايَٰتِ رَبِّهِمۡ إِلَّا كَانُواْ عَنۡهَا مُعۡرِضِينَ ٤ فَقَدۡ كَذَّبُواْ بِٱلۡحَقِّ لَمَّا
جَآءَهُمۡ فَسَوۡفَ يَأۡتِيهِمۡ أَنۢبَٰٓؤُاْ مَا كَانُواْ بِهِۦ يَسۡتَهۡزِءُونَ ٥ أَلَمۡ يَرَوۡاْ كَمۡ أَهۡلَكۡنَا مِن قَبۡلِهِم
مِّن قَرۡنٖ مَّكَّنَّٰهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ مَا لَمۡ نُمَكِّن لَّكُمۡ وَأَرۡسَلۡنَا ٱلسَّمَآءَ عَلَيۡهِم مِّدۡرَارٗا وَجَعَلۡنَا
ٱلۡأَنۡهَٰرَ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهِمۡ فَأَهۡلَكۡنَٰهُم بِذُنُوبِهِمۡ وَأَنشَأۡنَا مِنۢ بَعۡدِهِمۡ قَرۡنًا ءَاخَرِينَ ٦ وَلَوۡ نَزَّلۡنَا
عَلَيۡكَ كِتَٰبٗا فِي قِرۡطَاسٖ فَلَمَسُوهُ بِأَيۡدِيهِمۡ لَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ٧

**4-7.** ከጌታቸው አንቀፆች አንዱም አይመጣላቸውም እምቢ ብለው ከእርሱ የሚሸሹ ቢሆን እንጂ። (አጋሪዎች) እውነቱ (ቁርአን) በመጣላቸው ጊዜ በእርግጥ አስተባበሉ። ግን የእዚያ በእርሱ ይሳለቁበት የነበሩት ነገር ዜናዎች ቅጣት ይመጣባቸዋል። ከበፊታችሁ ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች መካከል ብዙዎቹን ማጥፋታችንን አላዩምን? ለእናንተ ያላስመቸነውን (ለእነርሱ) በምድር ውስጥ አስመቸናቸው። በእነርሱም ላይ ዝናብን የተከታተለ ሲሆን ላክን። ወንዞችንም በስራቸው እንዲፈሱ አደረግን። በኃጢአቶቻቸውም ምክንያት አጠፋናቸው። ከኋላቸውም ሌሎችን በየክፍለ ዘመን ሰዎች አስገኘን። በእነርሱ ላይ በወረቀት የተፃፈን መፅሐፍ ባወረድንና በእጆቻቸው በነኩት ኖሮ እነዚያ ከሓዲያን ይህ ግልፅ ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም ባሉ ነበር።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (7) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ የመካ ጣዖታውያን ወደ ነብዩ በመምጣት «ያንተን ጥሪ ሰምተን ኢስላምን ልንቀበል የምንችለው በአራት መላዕክት የታጀበ መፅሐፍ ስታመጣልን ብቻ ነው» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

وَقَالُواْ لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْهِ مَلَكٌۖ وَلَوْ أَنزَلْنَا مَلَكًا لَّقُضِيَ ٱلْأَمْرُ ثُمَّ لَا يُنظَرُونَ ﴿٨﴾
وَلَوْ جَعَلْنَٰهُ مَلَكًا لَّجَعَلْنَٰهُ رَجُلًا وَلَلَبَسْنَا عَلَيْهِم مَّا يَلْبِسُونَ ﴿٩﴾

**8-9.** በእርሱ (በሙሐመድ) ላይ መልአክ ለምን አይወረድለትም? አሉ። ነገር ግን መላዕክን ባወረድንም ኖሮ ባያምኑ የጥፋታቸው ነገሩ በተፈረደ ነበር። ከዚያ ኢሚንት አይቆዩም ነበር። መልዕክተኛውን ከመላዕክት መካከል ባደረግነው ኖሮ ወንድና በሰው ምስል አድርገን በመላክ በእነርሱ ላይ ባመሳሰልንባቸው ነበር።

وَلَقَدِ ٱسْتُهْزِئَ بِرُسُلٍ مِّن قَبْلِكَ فَحَاقَ بِٱلَّذِينَ سَخِرُواْ مِنْهُم مَّا كَانُواْ بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿١٠﴾ قُلْ
سِيرُواْ فِى ٱلْأَرْضِ ثُمَّ ٱنظُرُواْ كَيْفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلْمُكَذِّبِينَ ﴿١١﴾ قُل لِّمَن مَّا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِۖ
قُل لِّلَّهِۚ كَتَبَ عَلَىٰ نَفْسِهِ ٱلرَّحْمَةَۚ لَيَجْمَعَنَّكُمْ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ لَا رَيْبَ فِيهِۚ ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓاْ
أَنفُسَهُمْ فَهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٢﴾ ۞ وَلَهُۥ مَا سَكَنَ فِى ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ﴿١٣﴾

**10-13.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት በነበሩ ብዙ መልዕክተኞች ተላግጧል። እናም በእነዚያ ባላገጡት ሰዎች ላይ ያላገጡት ውጤት በእነርሱ ያላግጡት የነበሩት ነገር (ቅጣት) ወረደባቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ላይ ሂዱና የእነዚያን የአስተባባዮችን መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከቱ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የማን ነው? በላቸው። (ሌላ መልስ የለምና) የአላህ ብቻ ነው። አላህ በራሱ ላይ እዝነትን ፃፈ*። በዚያ በትንሳኤ ቀን ጥርጥር በሌለበት ይሰበስባችኋል። እነዚያ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩ ማለት እነርሱ ናቸው። እናም እነርሱም አያምኑም በላቸው። በሌሊትም ሆነ በቀን ፀጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። እርሱም ሰሚና አዋቂ ነው።

* የአላህን ረህመት ስፋት የሚያመለክቱ አያሌ ሐዲሶች መካከል፦ ቡኻሪ በዘገቡትና አቡ ሁረይራህ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ «አላህ እዝነቱን ወደ አንድ መቶ ከፋፈለውና ዘጠና ዘጠኙን ከእሱ ጋር አስቀምጦ አንዱን ክፍል ብቻ ወደ ምድር አወረደው። በዚህም አንድ ክፋይ የፈጠራቸው ፍጡራ እርስ በርሳቸው ይተዛዘናሉ። አንዲት ባዝራ ፈረስ እንኳ ውርንጭላዋን በኮቴዋ እንዳትረግጥ ኮቴዋን ወደ ላይ ታነሳለች»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ «አላህ መፍጠሩን ካጠናቀቀ በኋላ እርሱ ዘንድ ከዙፋኑ ጋር ባለው መፅሐፍ ላይ «እዝነቴ ቁጣዬን አሸነፈች» ሲል ፃፈ።»

قُلْ أَغَيْرَ ٱللَّهِ أَتَّخِذُ وَلِيًّا فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَهُوَ يُطْعِمُ وَلَا يُطْعَمُ ۗ قُلْ إِنِّىٓ أُمِرْتُ أَنْ أَكُونَ أَوَّلَ مَنْ أَسْلَمَ ۖ وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٤﴾ قُلْ إِنِّىٓ أَخَافُ إِنْ عَصَيْتُ رَبِّى عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ ﴿١٥﴾

**14-15.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰማያትና ምድርን ፈጣሪ ከሆነው አላህ እርሱ ፍጡርን የሚመግብና ለራሱ የማይመገብ አምላክ ሲሆን ሌላን አምላክ እይዛለሁን? እኔ መጀመሪያ ትዕዛዝን የተቀበለ ሰው እንድሆን ታዘዝኩ። ከአጋሪዎችም ፈፅሞ አትሁን (ተብያለሁ) በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ በጌታዬ ላይ ባምፅ የዚያን የታላቁን ቀን ቅጣት እፈራለሁ በላቸው።

مَّن يُصْرَفْ عَنْهُ يَوْمَئِذٍ فَقَدْ رَحِمَهُۥ ۚ وَذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْمُبِينُ ﴿١٦﴾ وَإِن يَمْسَسْكَ ٱللَّهُ بِضُرٍّ فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَ ۖ وَإِن يَمْسَسْكَ بِخَيْرٍ فَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿١٧﴾ وَهُوَ ٱلْقَاهِرُ فَوْقَ عِبَادِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلْحَكِيمُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٨﴾

**16-18.** በዚያ ቀን ከእርሱ ላይ ቅጣት የሚመለስለት ሰው በእርግጥ አላህ አዘነለት። ይህም በግልፅ እድለኝነት ማለት ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ችግር ቢያደርስብህ ከእርሱ በስተቀር ሌላ ማንም አስወጋጅ የለም። በጎ ነገርን ቢሰጥህ እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነው። እርሱ ከባሮቹ በላይ ሲሆን አሸናፊ ነው። እርሱ ጥበበኛና ውስጠ አዋቂ ነው።

قُلْ أَىُّ شَىْءٍ أَكْبَرُ شَهَٰدَةً ۖ قُلِ ٱللَّهُ ۖ شَهِيدٌۢ بَيْنِى وَبَيْنَكُمْ ۚ وَأُوحِىَ إِلَىَّ هَٰذَا ٱلْقُرْءَانُ لِأُنذِرَكُم بِهِۦ وَمَنۢ بَلَغَ ۚ أَئِنَّكُمْ لَتَشْهَدُونَ أَنَّ مَعَ ٱللَّهِ ءَالِهَةً أُخْرَىٰ ۚ قُل لَّآ أَشْهَدُ ۚ قُلْ إِنَّمَا هُوَ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ وَإِنَّنِى بَرِىٓءٌ مِّمَّا تُشْرِكُونَ ﴿١٩﴾

**19.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከምስክርነት ከነገሩ ሁሉ ይበልጥ ታላቁ የትኛው ነው? በላቸው። አላህ ነው:: በእኔና በእናንተ መካከል መስካሪ ነው በላቸው። ይህ ቁርኣን እናንተንና የደረሰውን ሰው ሁሉ ላስፈራራበት ወደ እኔ ተወረደ። ከአላህ ጋር ሌሎች አማልዕክት መኖራቸውን እናንተ ትመሰክራላቸሁን? በላቸው። እኔ ግን ፈፅሞ በዚህ አልመሰክርም በላቸው። እርሱ አንድ አምላክ ብቻ ነው። እኔም በአላህ ከምታጋሩት ነገራት ሁሉ ንፁህ ነኝ በላቸው።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (19) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ ሙሽሪኮች «ሙሐመድ ሆይ! የአንተን ጥሪ የተቀበለ አንድም ሰው አላገኘንም። አይሁድና ክርስቲያኖችንም ጠይቀን ስለ አንተ የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ነው ያስረዱን። ስለ አንተ ነብይነት የሚመሰክርልህ አንድ ሰው ጠቁመን አሳየን» በማለት ላቀረቡት በውሸት የተሞላ ጥያቄ ምላሽ ለመስጠት አላህ ያወረደው አንቀፅ ነው። የሚለውን ዘገባ ዋሒዲ የዘገቡት ሲሆን ሁለተኛውን ደግሞ «ሙሐመድ ሆይ! ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ እንዳለ አናውቅም» ሲሏቸው ነብዩ «ላኢላሀ ኢለላህ ማለት ታዲያ ይህ አይደለም እንዴ? የተላኩት ጥሪ የማደርገውስ ወደዚህ አይደለም እንዴ?» በማለት ሲናገሩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-19) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ አያሌ ውለታዎችን በእኛ ላይ የዋለ ጌታ መሆኑን፤
2. ይህንኑ አምኖ እርሱን ማመስገን ግዴታ መሆኑን፤
3. ማንኛውም ሰው ሊመሰገንባቸው የሚገቡ ባህርያት ሳይኖሩት ለመመስገን መቸኮል እንደማያስፈልግ፤
4. ፈጣሪንና ፍጡርን በአቻ የሚመለከቱ ሰዎች እጅግ እኩል ሊሆኑ የማይችሉ ነገሮችን እኩል ለማድረግ ቢሞክሩ ሞኛሞኞች በመሆናቸው ከሓዲነታቸው እንደሚንፀባረቅ፤
5. የአላህን ተአምራቶች ተመልክቶ ከሞተ በኋላ ህይወት መኖሩን የሚያስተባብል ሰው ግርምትን እንደሚያጭር፤
6. አላህ ሁሉን ነገር አዋቂ፤ በሰማይም ሆነ በምድር የሚከናወኑ ድርጊቶችን በሙሉ ግልፅና ድብቅ የሚመለከትና ከእርሱ እውቀት ውጭ ቅንጣት ያህል ነገር እንደሌለ፤
7. እውነትን ያለመቀበል የሚያስከትለው መዘዝ የከፋ መሆኑን፤
8. በሃይማኖት ላይ ማፌዝና በድንጋጌዎቹም ላይ ማላገጥ ለአስቃቂ ቅጣት የሚዳርግ ወንጀል መሆኑን፤
9. ማንኛውም የቁርኣን አንቀፅ ሲቀርብለት የሚሸሽ ሰው ቀልቡን ለእምነት ያላዘጋጀ ሰው መሆኑን፤
10. በወንጀላቸው ምክንያት አላህ ቁጣውን በመላክ ያጠፋቸውን ሰዎች ታሪክ በማስታወስና ከግፈኞች ውድቀት መማር እንዳለብን፤
11. የቀደምት ነብያት ህዝቦች የነበሩ የተለያዩ ትውልዶች የአላህ ቁጣ የወረደባቸውና የጠፉት በሰሩት ወንጀል ምክንያት እንደነበር፤
12. ለችግሮቻችን ብቸኛው መፍትሔ ሰጪ አላህ ብቻ ስለመሆኑ፤
13. በጎም ሆነ ጎጂ አጋጣሚ ከአላህ እንደሆነ፤
14. ነብዩ የአላህ መልእክተኛ መሆናቸውን በተመለከተ ራሱ ምስክርነት መስጠቱ፤
15. አላህ በፈጣሪነት ብቻ ሳይሆን በአምላክነትም ብቸኛ መሆኑንና በተመላኪነቱም ብቸኛ እንደሆነ እንማራለን።

ٱلَّذِينَ ءَاتَيْنَٰهُمُ ٱلْكِتَٰبَ يَعْرِفُونَهُۥ كَمَا يَعْرِفُونَ أَبْنَآءَهُمُ
ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓا۟ أَنفُسَهُمْ فَهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿٢٠﴾

**20.** እነዚያ መጽሐፍን የሰጠናቸው (አይሁዶች) ልክ ልጆቻቸውን እንደሚያውቁ ሁሉ ሙሐመድንም ያውቁታል። እነዚያ ከእነርሱ ውስጥ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩት ከፍሎች ፈፅሞ አያምኑም።

وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِـَٔايَٰتِهِۦٓ ۗ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٢١﴾
وَيَوْمَ نَحْشُرُهُمْ جَمِيعًا ثُمَّ نَقُولُ لِلَّذِينَ أَشْرَكُوٓاْ أَيْنَ شُرَكَآؤُكُمُ ٱلَّذِينَ كُنتُمْ تَزْعُمُونَ ﴿٢٢﴾
ثُمَّ لَمْ تَكُن فِتْنَتُهُمْ إِلَّآ أَن قَالُواْ وَٱللَّهِ رَبِّنَا مَا كُنَّا مُشْرِكِينَ ﴿٢٣﴾ ٱنظُرْ كَيْفَ كَذَبُواْ عَلَىٰٓ
أَنفُسِهِمْ ۚ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُواْ يَفْتَرُونَ ﴿٢٤﴾

**21-24.** በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ወይም በአናቅፅ ካስተባበለ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማን ነው? እነሆ በደለኞች ሁሉ ከአላህ ቅጣት አይድኑም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁላቸውንም በምንሰበስብበትና ከዚያ ለእነዚያ ጣዖትን በአላህ ላጋሩት፤ እነዚያ ለአላህ ተጋሪዎች ናቸው ብላችሁ ታስቧቸው የነበሩት ተጋሪዎቻችሁ የት ናቸው? የምንልበትን ቀን (አስታውስ)። ከዚያም መልሳቸው በጌታችን በአላህ ይሁንብን አጋሪዎች አልነበርንም ማለት እንጂ ሌላ አይሆንም። በነፍሶቻቸው ላይ እንዴት እንደዋሹና ይቀጣጥፉት የነበሩት ነገር ሁሉ ከእነርሱ እንዴት እንደተሰወረባቸው ተመልከት።

وَمِنْهُم مَّن يَسْتَمِعُ إِلَيْكَ ۖ وَجَعَلْنَا عَلَىٰ قُلُوبِهِمْ أَكِنَّةً أَن يَفْقَهُوهُ وَفِىٓ ءَاذَانِهِمْ وَقْرًا ۚ وَإِن
يَرَوْاْ كُلَّ ءَايَةٍ لَّا يُؤْمِنُواْ بِهَا ۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءُوكَ يُجَٰدِلُونَكَ يَقُولُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِنْ هَٰذَآ
إِلَّآ أَسَٰطِيرُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿٢٥﴾ وَهُمْ يَنْهَوْنَ عَنْهُ وَيَنْـَٔوْنَ عَنْهُ ۖ وَإِن يُهْلِكُونَ إِلَّآ أَنفُسَهُمْ وَمَا
يَشْعُرُونَ ﴿٢٦﴾ وَلَوْ تَرَىٰٓ إِذْ وُقِفُواْ عَلَى ٱلنَّارِ فَقَالُواْ يَٰلَيْتَنَا نُرَدُّ وَلَا نُكَذِّبَ بِـَٔايَٰتِ رَبِّنَا
وَنَكُونَ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٢٧﴾

**25-27.** ከእነርሱ መካከል ወደ አንተ የሚያዳምጥ ሰው አለ። በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሽፋኖችን፤ በጆሮዎቻቸው ላይ እንዳይሰሙት ድንቁርናን አደረግን። ተዐምርን ሁሉ ቢያዩ በእርሷ አያምኑም። ወደ አንተ በመጡ ጊዜ የሚከራከሩህ ሲሆኑ እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ይህ ቁርኣን የቀድሞዎቹ ሰዎች ፁሑፍ ተረቶች ስብስብ እንጂ ሌላ አይደለም ይላሉ። እነርሱም ሰዎችን ከእርሱ ይከለክላሉ፤ ከእርሱም ይርቃሉ፤ በዚህ ተግባራቸው ነፍሶቻቸውን እንጂ ሌላን አያጠፉም። ግን አያውቁም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእሳት ላይ እንዲቆሙ በተደረጉ ጊዜ ምን ነው ወደ ምድረ ዓለም በተመለስንና በጌታችን አንቀፆች ባላስተባበልን ከትክክለኛ ምዕመናንም ጋር በሆንን ዋ! ምኞታችን ባሉ ጊዜ ብታይ ኖሮ (የሚያስደነግጥህን ነገር ባየህ ነበር።)

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (25) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡሱፍያን ኢብኑ ሀርብ፤ ወሊድ ቢን ሙጊራህ፤ ነዷር ቢን ሐሪስ እና ሌሎችም ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ሳለ ነብዩ (ﷺ) ቁርኣንን ሲያነቡ ሰሟቸው። እነሱም ለጓደኛቸው ለነዷር «እስቲ ስለዚህ (የቁርኣን ንባብ) ምን ትላለህ?» በማለት ጠየቁት። እርሱም «ይሄማ ከዚህ በፊት እንደነገርኳችሁ የድሮ ሰዎች ተረት ተረት ነው ሙሐመድ የሚያነበው። እኔ እኮ ከንፈሩን ሲያነቃንቅ እንጂ ምን ቁም ነገር እንደተናገረ አልሰማሁትም። እኔ ያለፉትን ዘመናት ታሪክ እነግራችሁ እንደነበረው ሁሉ ነው የሚነግራችሁ» በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑል -ጀውዚ እና ሱዩጢ)

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (26) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ለነብዩ ይከላከሉ የነበሩት ነገር ግን የሚያስተምሩትን ባላመኑት አጎታቸው በአቡጧሊብ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ፤ ኢብኑ-ል ጀውዚ እና ሱዩጢ)።

بَلۡ بَدَا لَهُم مَّا كَانُواْ يُخۡفُونَ مِن قَبۡلُۖ وَلَوۡ رُدُّواْ لَعَادُواْ لِمَا نُهُواْ عَنۡهُ وَإِنَّهُمۡ لَكَٰذِبُونَ ٢٨
وَقَالُوٓاْ إِنۡ هِيَ إِلَّا حَيَاتُنَا ٱلدُّنۡيَا وَمَا نَحۡنُ بِمَبۡعُوثِينَ ٢٩ وَلَوۡ تَرَىٰٓ إِذۡ وُقِفُواْ عَلَىٰ رَبِّهِمۡۚ قَالَ
أَلَيۡسَ هَٰذَا بِٱلۡحَقِّۚ قَالُواْ بَلَىٰ وَرَبِّنَاۚ قَالَ فَذُوقُواْ ٱلۡعَذَابَ بِمَا كُنتُمۡ تَكۡفُرُونَ ٣٠

**28-30.** ከዚህ በፊት ይደብቁት የነበሩት ነገር ሁሉ ለእነርሱ ተገለፀ። ወደ ምድረ ዓለም በተመለሱም ኖሮ ወደ ተከለከሉት ነገር በተመለሱ ነበር። እነርሱ ሐሰተኞች ናቸውና። ሕይወት ማለት ቅርቢቱ ሕይወታችን እንጂ ሌላ አይደለችም። እኛም ፈፅሞ ተቀስቃሾች አይደለንም አሉ። (ሙሐመድ ሆይ!) በጌታቸው ዘንድ ለምርመራ እንዲቆሙ በተደረጉ ጊዜ ብታይ ኖሮ (አስደንጋጭን ነገር ባየህ ነበር)። ይህ እውነት አይደለምን? ይላቸዋል። እነርሱም በጌታችን ይሁንብን እውነት ነው ይላሉ። እናም ትክዱት በነበራችሁት ምክንያት ቅጣቱን ቅመሱ ይላቸዋል።

قَدۡ خَسِرَ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِلِقَآءِ ٱللَّهِۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَتۡهُمُ ٱلسَّاعَةُ بَغۡتَةٗ قَالُواْ يَٰحَسۡرَتَنَا عَلَىٰ مَا
فَرَّطۡنَا فِيهَا وَهُمۡ يَحۡمِلُونَ أَوۡزَارَهُمۡ عَلَىٰ ظُهُورِهِمۡۚ أَلَا سَآءَ مَا يَزِرُونَ ٣١ وَمَا ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَآ
إِلَّا لَعِبٞ وَلَهۡوٞۖ وَلَلدَّارُ ٱلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ لِّلَّذِينَ يَتَّقُونَۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ٣٢

**31-32.** እነዚያ ከአላህ* ጋር መገናኘትን ያስተባበሉ ሰዎች ሁሉ ከሰሩ። ሰዓቲቱ በድንገት በመጣችባቸው ጊዜ እነርሱ ኃጢአቶቻቸውን በጀርባዎቻቸው ላይ የሚሸከሙ ሲሆኑ በምድረ ዓለም ባጓደልነው ነገር ላይ ዋ! ጥፋታችን፤ (ቁጭታችን) ይላሉ። (ሙስሊሞች ሆይ) ንቁ፣ ያ፣ የሚሸከሙት ነገር ምንኛ ከፋ። የቅርቢቱ ሕይወት ማለት ጨዋታና ላግጣ እንጂ ሌላ አይደለችም። የመጨረሻይቱ አገር ገነት ግን ለእነዚያ ለሚጠነቀቁት ሰዎች ሁሉ በጣም በላጭ ናት። አታውቁምን? (አትገነዘቡምን)?

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከአላህ ጋር መገናኘት የሚወድን ሰው አላህ ከእሱ ጋር መገናኘትን በጣም ይወድለታል። እንደዚሁም ከአላህ ጋር መገናኘትን የሚጠላ ሰው አላህም ከርሱ ጋር መገናኘትን በጣም ይጠላል»

قَدْ نَعْلَمُ إِنَّهُۥ لَيَحْزُنُكَ ٱلَّذِى يَقُولُونَ ۖ فَإِنَّهُمْ لَا يُكَذِّبُونَكَ وَلَٰكِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ
يَجْحَدُونَ ﴿٣٣﴾ وَلَقَدْ كُذِّبَتْ رُسُلٌ مِّن قَبْلِكَ فَصَبَرُوا۟ عَلَىٰ مَا كُذِّبُوا۟ وَأُوذُوا۟ حَتَّىٰٓ أَتَىٰهُمْ
نَصْرُنَا ۚ وَلَا مُبَدِّلَ لِكَلِمَٰتِ ٱللَّهِ ۚ وَلَقَدْ جَآءَكَ مِن نَّبَإِى۟ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿٣٤﴾ وَإِن كَانَ كَبُرَ عَلَيْكَ
إِعْرَاضُهُمْ فَإِنِ ٱسْتَطَعْتَ أَن تَبْتَغِىَ نَفَقًا فِى ٱلْأَرْضِ أَوْ سُلَّمًا فِى ٱلسَّمَآءِ فَتَأْتِيَهُم بِـَٔايَةٍ ۚ وَلَوْ
شَآءَ ٱللَّهُ لَجَمَعَهُمْ عَلَى ٱلْهُدَىٰ ۚ فَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْجَٰهِلِينَ ﴿٣٥﴾

**33-35.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያ፣ የሚሉህ ነገር እንደሚያሳዝንህ በእርግጥ እናውቃለን። እነርሱ በእርግጥ ልቦቻቸው አያስተባብሉህም። ግን በዳዮች ሁሉ የአላህን አንቀፆች ይክዳሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከበፊትህ የነበሩት መልዕክተኞች ተስተባብለዋል። በተስተባበሉበትም ነገርና በተሰቃዩት ላይ እርዳታችን እስከመጣላቸው ድረስ ታገሱ። የአላህን ቃላት የሚለውጥ ማንም የለም። ከመልዕክተኞቹም ወሬ (የምትረጋጋበት) በእርግጥ መጣልህ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢስላምን መተዋቸው በአንተ ላይ ከባድ ቢሆንም በምድር ውስጥ ቀዳዳን ወይም በሰማይ ውስጥ መሰላልን ልትፈልግና ተአምር ልታመጣላቸው ብትችል (አድርግ) አላህ በፈለገ ኖሮ ሁሉንም በቅኑ መንገድ ላይ በሰበሰባቸው ነበር። ከተሳሳቱት ሰዎች በፍፁም አትሁን።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (33) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት ተብለው ከተወሩት መካከል፡- አኽነስ ቢን አሸረቅና እና አቡ. ጀህል ቢን ሂሻም አንድ ቦታ ተገኛኝተው እያወሩ ሳለ አኽነስ ለአቡ. ጀህል «እስኪ ስለ ሙሐመድ አጫውተኝ። ሙሐመድ ውሸታም ነው ወይስ እውነተኛ እባክህ እውነቱን ንገረኝ» በማለት ይጠየቃሉ። አቡጀህልም «አሁን ከእኛ ሌላ ማንም ሰው የለምና እውነቱን ልንገርህ። ሙሐመድ እውነተኛና አንድም ቀን ዋሽቶ የማያውቅ ሰው ነው። ነገር ግን ከቁረይሽ ጎሳ ውስጥ የቁሰይ ልጆች የበነብዩ (ﷺ) ቅድመ አያት ልጆች ማለት ነው። ነብይነት፤ ባንዲራንና መስተንግዶን እንዲሁም የመካን ጥበቃ ከወሰዱ ሌላ የቁረይሽ ዘር ምን ይኖረዋል? ስለዚህም እኛ በእርሱ እንዋጣለን» በማለቱና ለስሜቱና ለስልጣን ፍለጋ የሚቃወማቸው መሆኑን እራሱ በማጋለጡ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (20-35) ከምናገኛቸው እንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አህለል ኪታቦች ሙሐመድን (ﷺ) እንደ ወንዶች ልጆቻቸው አበጥረው እያወቁ ባለማመን ነፍሶቻቸውን ስላከሰሩ አምነው ሊቀበሉ ያለመቻላቸውን፤
2. የመፅሐፍ ሰዎች (አይሁዶችና ክርስቲያኖች) ኢስላምን እንዳይቀበሉ ዋነኛ እንቅፋት የሆነባቸው ነገር ምድራዊ ምቾትንና ጥቅምን ከአኼራ ማስበለጣቸው እንደነበር፤

3. በአላህ እንዲሁም በቁርኣን አናቅፅ ላይ ውሸትን መቅጠፍ የሚያስከትለው ቅጣት እጅግ ከባድ መሆኑን፤
4. የግፍ አራማጅ አመፀኞችና ወንጀለኞች በምድራዊው ህይወት ቆይታቸውም ሆነ ነገ ከሞት በኋላ ባለው አኼራዊ ህይወት ጥሩ እድል እንደማይገጥማቸው፤
5. ሁሉም ፍጥረት የሚሰበሰብበት ቀን እንዳለና ጣኦት አምላኪዎች በአደባባይ ለጥያቄ የሚቀርቡበት እለት መሆኑን እነሱም በታላቁ ቀን ከማስተባበል ውጪ አጥጋቢ መልስ እንደማይኖራቸው
6. የሌሎች ሰዎች ጥላቻ በልቡ ያደረበት ሰው የጠላቸውን ሰዎች ንግግር ለመስማት እንኳን እንደማይፈቀድና ግልፅ ማብራሪያ ቢሰጡትም ለመረዳት እንደሚቸገር፤
7. እውነትን አለመቀበሉ ሳይበቃው ሌሎች እውነትን እንዳይቀበሉ የሚሞከር ሰው ከመጥፎዎች ሁሉ መጥፎ ሰው መሆኑን፤
8. ከሞት በኋላ ደግሞ መነሳትና ለጥያቄ መቅረብ የማይቀር ሐቅ መሆኑን ማረጋገጥ፤
9. ወንጀል አስቀያሚና ለህሊናም እጅግ የሚከብድ ሸክም መሆኑን፤
10. ሙቶ መቀስቀስ ሐቅ መሆኑን ሳይቀበልና ለወዲያኛውም ዓለም የሚሆነውን መልካም ስንቅ ሳይዝ በሞት የተቀደመ ሰው እጅግ ከፍ ያለ ኪሳራ ውስጥ እንደተዘፈቀ፤
11. አዕምሮ ያላቸው ሰዎች በዱንያ እንዳይታለሉና አኼራን እንዳይዘነጉ ቁርኣን ምክር ማስተላለፉን፤ ቂያማ በቀነ ቀጠሮ የተገደበ ሳይሆን አላህ በፈለገው ቀን በድንገት የሚወሰነው መሆኑን፤
12. ነብዩ (ﷺ) የሰው ልጅ እንደነበሩ ቁርኣናዊ ማረጋገጫ መስጠቱን፤
13. የአላህን ጌትነት የነብዩን መልዕክተኝነት እና ከሞት በኋላ ህይወት መኖሩን ከልብ አምኖ መቀበል የመኖር ትርጉም የሚለይበት መሆኑንና በአንፃሩ ግን በእነዚህ መሠረታዊ ነገሮች ያለማመን የህይወትን አላማ ያለመገንዘብ እና መንፈሳዊ ሞት መሆኑን፤
14. ከሓዲያን ነብዩ (ﷺ) እንዲያሳዩዋቸው የጠየቋአቸውን ተዐምራት አላህ ያላሳያቸው እነዚህ ከሓዲያን ተአምራቶቹን ቢያዩም እንደማያምኑ ብሎም ለአላህ ቅጣት የበለጠ እንደሚጋለጡ ስለሚያውቅ እንደሆነ፤
15. በምድር ላይ ያሉ ፍጡራን አይነታቸው የበዛ ቁጥራቸውም በዚያው ልክ እጅግ ብዙ መሆኑን፤
16. ቀደና ቀደር የአላህ ውሳኔን መቀበል ከእምነት ዘርፎች የሚካተት መሆኑን እንማራለን።

۞ إِنَّمَا يَسْتَجِيبُ ٱلَّذِينَ يَسْمَعُونَ وَٱلْمَوْتَىٰ يَبْعَثُهُمُ ٱللَّهُ ثُمَّ إِلَيْهِ يُرْجَعُونَ ﴿٣٦﴾ وَقَالُوا۟ لَوْلَا نُزِّلَ
عَلَيْهِ ءَايَةٌ مِّن رَّبِّهِۦ ۚ قُلْ إِنَّ ٱللَّهَ قَادِرٌ عَلَىٰٓ أَن يُنَزِّلَ ءَايَةً وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٧﴾

**36-37.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጥሪህን የሚቀበሉህ እነዚያ የሚሰሙት ብቻ ናቸው። ሙታንን አላህ ይቀሰቅሳቸዋል። ከዚያም ወደ እርሱ ብቻ ይመለሳሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲያን ከጌታው በእርሱ ላይ ለምን ተአምር አልተወረደለትም አሉ። አላህ ተአምርን ለማውረድ ቻይ ነው። ግን አብዛኞቻቸው ይህን እውነታ አያውቁም በላቸው።

وَمَا مِن دَآبَّةٍ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا طَٰٓئِرٍ يَطِيرُ بِجَنَاحَيۡهِ إِلَّآ أُمَمٌ أَمۡثَالُكُمۚ
مَّا فَرَّطۡنَا فِي ٱلۡكِتَٰبِ مِن شَيۡءٖۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّهِمۡ يُحۡشَرُونَ ﴿٣٨﴾

**38.** በምድር ላይም የሚሄድ ተንቀሳቃሽ ተንቀሳቃሽም ሆነ በሁለት ክንፎች የሚበር ሁሉ መሰሎቻችሁ ሕዝቦች እንጂ ሌላ አይደሉም። በመጽሐፍ ውስጥ ምንንም ነገር አልተውንም። ከዚያ ሁሉም ወደ ጌታቸው ይሰበሰባሉ።

وَٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا صُمّٞ وَبُكۡمٞ فِي ٱلظُّلُمَٰتِۗ مَن يَشَإِ ٱللَّهُ يُضۡلِلۡهُ
وَمَن يَشَأۡ يَجۡعَلۡهُ عَلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ﴿٣٩﴾

**39.** እነዚያ በአንቀፆቻችን ያስተባበሉ ሰዎች ሁሉ እውነትን የማይሰሙ ደንቆሮዎች፣ ሐቅን ደፍረው የማይናገሩ ዲዳዎችና በጨለማዎች ውስጥ ያሉ ናቸው። አላህ መጥመሙን የሚሻውን (የሚሻበትን) ሰው ያጠመዋል። ወደ ቀናው መንገድ መመራቱን የሚሻውን ሰው ደግሞ በቀጥተኛው መንገድ ላይ እንዲሄድ ያደርገዋል።

قُلۡ أَرَءَيۡتَكُمۡ إِنۡ أَتَىٰكُمۡ عَذَابُ ٱللَّهِ أَوۡ أَتَتۡكُمُ ٱلسَّاعَةُ أَغَيۡرَ ٱللَّهِ تَدۡعُونَ إِن كُنتُمۡ
صَٰدِقِينَ ﴿٤٠﴾ بَلۡ إِيَّاهُ تَدۡعُونَ فَيَكۡشِفُ مَا تَدۡعُونَ إِلَيۡهِ إِن شَآءَ وَتَنسَوۡنَ مَا تُشۡرِكُونَ ﴿٤١﴾

**40-41.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የአላህ ቅጣት ቢመጣባችሁ ወይም ትንሳኤ ብትመጣባችሁ ከአላህ ሌላ ትጠራላችሁን? እውነተኞች ከሆናችሁ እስኪ ንገሩኝ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አይደለም እርሱን ብቻ ትጠራላችሁ። ቢሻ ወደ እርሱ የምትጠሩበትን ነገር ያስወግድላችኋልና የምታጋሩትን ነገር ሁሉ ትተዋላችሁ በላቸው።

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَآ إِلَىٰٓ أُمَمٖ مِّن قَبۡلِكَ فَأَخَذۡنَٰهُم بِٱلۡبَأۡسَآءِ وَٱلضَّرَّآءِ لَعَلَّهُمۡ يَتَضَرَّعُونَ ﴿٤٢﴾ فَلَوۡلَآ
إِذۡ جَآءَهُم بَأۡسُنَا تَضَرَّعُواْ وَلَٰكِن قَسَتۡ قُلُوبُهُمۡ وَزَيَّنَ لَهُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿٤٣﴾
فَلَمَّا نَسُواْ مَا ذُكِّرُواْ بِهِۦ فَتَحۡنَا عَلَيۡهِمۡ أَبۡوَٰبَ كُلِّ شَيۡءٍ حَتَّىٰٓ إِذَا فَرِحُواْ بِمَآ أُوتُوٓاْ أَخَذۡنَٰهُم
بَغۡتَةٗ فَإِذَا هُم مُّبۡلِسُونَ ﴿٤٤﴾ فَقُطِعَ دَابِرُ ٱلۡقَوۡمِ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْۚ وَٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٤٥﴾

**42-45.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት ለነበሩት ሕዝቦች መልዕክተኞችን በእርግጥ ላክን፡፡ ለእኛ ይተናነሱም ዘንድ በድህነትና በችግር ቀጣናቸው፡፡ ታዲያ ቅጣታችን በመጣባቸው ጊዜ ለምን አይተናነሱም ኖሯል? ነገር ግን ይባስ ብሎ ልቦቻቸው ደረቁ፡፡ ይሰሩት የነበሩትንም መጥፎ ነገር ሁሉ ሰይጣን መልካም ነገር አስመስሎ አሳያቸው፡፡ በእርሱ ይገሰፁበት የነበረውን ነገር በዘነጉ ጊዜ ለእነርሱ የሁሉን ነገር ደጃፎችን ከፈትንላቸውና በኑሮ አስመቸናቸው፡፡ በተሰጡትም ነገር በተደሰቱ ጊዜ በድንገት ቀጣናቸው፡፡ ወዲያውኑም እነርሱ ተስፋ ቆራጮች ሆኑ፡፡ የእነዚያ የበደሉት ሕዝቦች መጨረሻ ተቆረጠ፡፡ ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይገባው፡፡

**ከቤት እንስሳት ምዕራፍ ከአንቀፅ (36-44) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሓዲያን እውነትን ባለመስማታቸው በሙታን እንደሚመሰሉ፤
2. ከሓዲያን የጠየቁቱን ተዐምር አላህ ያለማውረዱ ምክንያት ቅጣትን እንዳያፋጥንባቸው መሆኑን፤
3. አላህ ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል መሆኑን፤
4. አላህ የፈጠራቸው ሁሉ እንደሰዎች ሁሉ በአላህ የተፈጠሩና ሁለንተናቸውን የሚያስተናብርላቸው በመሆኑ ከእኛ ጋር ተመሳሳይነት እንዳላቸው፤
5. በአላህ ችሮታ ልንሸነገል እንደማይገባ እንማራለን፡፡

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِنۡ أَخَذَ ٱللَّهُ سَمۡعَكُمۡ وَأَبۡصَٰرَكُمۡ وَخَتَمَ عَلَىٰ قُلُوبِكُم مَّنۡ إِلَٰهٌ غَيۡرُ ٱللَّهِ
يَأۡتِيكُم بِهِۗ ٱنظُرۡ كَيۡفَ نُصَرِّفُ ٱلۡأٓيَٰتِ ثُمَّ هُمۡ يَصۡدِفُونَ ﴿٤٦﴾ قُلۡ أَرَءَيۡتَكُمۡ إِنۡ أَتَىٰكُمۡ
عَذَابُ ٱللَّهِ بَغۡتَةً أَوۡ جَهۡرَةً هَلۡ يُهۡلَكُ إِلَّا ٱلۡقَوۡمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٤٧﴾

**46-47.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እስቲ ንገሩኝ አላህ መስሚያችሁንና ማያዎቻችሁን ቢወስድባችሁና በልቦቻችሁ ላይ ቢያትም ከአላህ ሌላ የሚያመጣላችሁ አምላክ ማን ነው? በላቸው፡፡ አንቀፆችን እንዴት እንደምናብራራና ከዚያ እነርሱ እንዴት መንገዱን እንደሚስቱ ተመልከት፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እስቲ ንገሩኝ የአላህ ቅጣት ድንገት ወይም በግልፅ ቢመጣባችሁ ከአመፀኛ ህዝቦች ሌላ ይጠፋልን? በላቸው፡፡

وَمَا نُرۡسِلُ ٱلۡمُرۡسَلِينَ إِلَّا مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَۖ فَمَنۡ ءَامَنَ وَأَصۡلَحَ فَلَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ
وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ﴿٤٨﴾ وَٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا يَمَسُّهُمُ ٱلۡعَذَابُ بِمَا كَانُواْ يَفۡسُقُونَ ﴿٤٩﴾

**48-49.** ሁሉንም መልዕክተኞችን በመልካም አብሳሪና ከመጥፎ አስፈራሪ አድርገን እንጂ አንልክም። እናም በእነርሱ ያመኑና በጎን ተግባር የሰሩት ሰዎች ሁሉ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለውም አያዝኑምም። እነዚያ አንቀፆቻችንን ያስተባበሉ ሰዎች ሁሉ በአመፃቸው ምክንያት ቅጣት ያገኛቸዋል።

قُل لَّآ أَقُولُ لَكُمۡ عِندِي خَزَآئِنُ ٱللَّهِ وَلَآ أَعۡلَمُ ٱلۡغَيۡبَ وَلَآ أَقُولُ لَكُمۡ إِنِّي مَلَكٌۖ
إِنۡ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّۚ قُلۡ هَلۡ يَسۡتَوِي ٱلۡأَعۡمَىٰ وَٱلۡبَصِيرُۚ أَفَلَا تَتَفَكَّرُونَ ٥٠

**50.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለናንተ የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልላችሁም። ሩቅ ሚስጥርንም አላውቅም። ለናንተም መላዕክት ነኝም አልልም። ወደ እኔ የሚወርድልኝን መልዕክት እንጂ ሌላን አልከተልም በላቸው። እውርና የሚያይ ይስተካከላሉን? አታስተነትኑምን! በላቸው።

وَأَنذِرۡ بِهِ ٱلَّذِينَ يَخَافُونَ أَن يُحۡشَرُوٓاْ إِلَىٰ رَبِّهِمۡ لَيۡسَ لَهُم مِّن دُونِهِۦ وَلِيّٞ وَلَا شَفِيعٞ
لَّعَلَّهُمۡ يَتَّقُونَ ٥١ وَلَا تَطۡرُدِ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ رَبَّهُم بِٱلۡغَدَوٰةِ وَٱلۡعَشِيِّ يُرِيدُونَ وَجۡهَهُۥۖ مَا
عَلَيۡكَ مِنۡ حِسَابِهِم مِّن شَيۡءٖ وَمَا مِنۡ حِسَابِكَ عَلَيۡهِم مِّن شَيۡءٖ فَتَطۡرُدَهُمۡ فَتَكُونَ مِنَ
ٱلظَّٰلِمِينَ ٥٢ وَكَذَٰلِكَ فَتَنَّا بَعۡضَهُم بِبَعۡضٖ لِّيَقُولُوٓاْ أَهَٰٓؤُلَآءِ مَنَّ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مِّنۢ بَيۡنِنَآۗ
أَلَيۡسَ ٱللَّهُ بِأَعۡلَمَ بِٱلشَّٰكِرِينَ ٥٣

**51-53.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ከአላህ ሌላ ወዳጅና አማላጅ የሌላቸው ሲሆኑ ወደ ጌታቸው መሰብሰብን የሚፈሩትን ሰዎች ይጠነቀቁ ዘንድ በቁርኣን አስፈራራ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን የጌታቸውን ውዴታን የሚሹ ሆነው በጧትና በማታ የሚጠሩትን አማኞች ከአጠገብህ አታባር። ታባርራቸውና ከበደለኞች ትሆናለህ። እነርሱን መቆጣጠር ባንተ ላይ ግዴታ የለብህም። አንተንም መቆጣጠር በነሱ ላይ ምንም የለባቸውም (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልክ እንደዚሁም ከመካከላችን አላህ በእነርሱ ላይ ችሮታውን የለገሳቸው እነዚህ ናቸውን? ይሉ ዘንድ ከፊላቸውን በከፊሎች ሞከርን። አላህ አመስጋኞቹን ከሁሉም በላይ አዋቂ አይደለምን?

**ከቤት እንስሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (45-52) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን ብቸኝነት የሚያሳዩ ተዐምራቶች ብዙ ቢሆኑም ከሓዲያን ይህንን ሁሉ እምቢ ብለው እንደካዱ፤
2. የነብያት ኃላፊነት ማብሰርና ማስፈራራት እንደሆነ፤
3. ነብዩ (ﷺ) አላህ ያሳወቃቸውን እንጂ ድብቅን ነገር እንደማያውቁ፤
4. ጣኦት አምላኪዎች ለነብዩ (ﷺ) ከአቅማቸው በላይ ጥያቄዎችን እያቀረቡ ያስቸግሯቸው እንደነበር፤
5. ትክክለኛ አማኞች በቁርአንና በአስተምህሮቱ ተጠቃሚ እንደሆኑን ከሓዲያን ግን ተጠቃሚዎች እንዳልሆኑ፤
6. የሰው ልጆች እኩል እንደሆኑ በሀብት፤ በስልጣን ምክንያት ያሉት ልዩነቶች ከአላህ ዘንድ ምንም ዋጋ እንደሌላቸው፤

وَإِذَا جَآءَكَ ٱلَّذِينَ يُؤۡمِنُونَ بِـَٔايَٰتِنَا فَقُلۡ سَلَٰمٌ عَلَيۡكُمۡۖ كَتَبَ رَبُّكُمۡ عَلَىٰ نَفۡسِهِ ٱلرَّحۡمَةَ
أَنَّهُۥ مَنۡ عَمِلَ مِنكُمۡ سُوٓءَۢا بِجَهَٰلَةٖ ثُمَّ تَابَ مِنۢ بَعۡدِهِۦ وَأَصۡلَحَ فَأَنَّهُۥ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٥٤
وَكَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ وَلِتَسۡتَبِينَ سَبِيلُ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ٥٥

**54-55.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በተዐምራታችን የሚያምኑት ሰዎች ሁሉ ወደ አንተ በመጡ ጊዜ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን። ጌታችን በነፍሱ (በራሱ) ላይ እዝነት ፃፈ። እነሆ ከናንተ ውስጥ ስህተት ስራ የሰራ ሰውና ከዚያ የተፀፀተና ወዲያውኑ ስራውን ያሳመረ ሰው ሁሉ እርሱ አላህ መህሪና አዛኝ ነውና በላቸው። እንደዚሁም እውነቱ እንዲገለፅና የወንጀለኞች መንገድ ትብራራ ዘንድ አንቀፆችን እንገልፃለን።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከ (52-54) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከእነ ቢላል፤ ሱሐይብ፤ ኸባብና አማር ጋር ተቀምጠው ሳለ የቁረይሽ መሪዎችና አለቆች ከአጠገባቸው እያለፉ ሳሉ እንዲህ አሏቸው «ሙሐመድ ሆይ! ከእኛ ከስጋ ዘመዶችህ ይልቅ እነኚህ ተሻሉህን? እኛንስ የምትጠራን የእነርሱ ተከታዩች ልታደርገን ነውን? ደሞስ አላህ የመረጣቸው እያልክ የምታወድሳቸውስ እነዚህን ነውን? በማለት እያጥላሉ ተናገሩና በመቀጠል «እነሱን ካላባረርካቸው ያንተን ጥሪ ልንሰማና ልናምንህ አንችልም» በማለታቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

قُلۡ إِنِّي نُهِيتُ أَنۡ أَعۡبُدَ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِۚ قُل لَّآ أَتَّبِعُ أَهۡوَآءَكُمۡ قَدۡ ضَلَلۡتُ إِذٗا
وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلۡمُهۡتَدِينَ ٥٦ قُلۡ إِنِّي عَلَىٰ بَيِّنَةٖ مِّن رَّبِّي وَكَذَّبۡتُم بِهِۦۚ مَا عِندِي مَا تَسۡتَعۡجِلُونَ
بِهِۦٓۚ إِنِ ٱلۡحُكۡمُ إِلَّا لِلَّهِۖ يَقُصُّ ٱلۡحَقَّۖ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلۡفَٰصِلِينَ ٥٧ قُل لَّوۡ أَنَّ عِندِي مَا
تَسۡتَعۡجِلُونَ بِهِۦ لَقُضِيَ ٱلۡأَمۡرُ بَيۡنِي وَبَيۡنَكُمۡۗ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِٱلظَّٰلِمِينَ ٥٨

**56-58.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ እነዚያን ከአላህ ሌላ የምትጠሯቸውን ባዕድ አማልክት ከመገዛት ተከልክያለሁ በላቸው። ዝንባሌያችሁን አልከተልም። ያን ካደረኩኝ በእርግጥ ተሳሳትኩ። እኔም ከተመሪዎች አይደለሁም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሰዎች ሆይ)፣ እኔ ከጌታዬ በመጣልኝ ግልፅ ማስረጃ ላይ ነኝ። (እናንተ ግን) በእርሱ አስተባበላችሁ። ያ የምትቻኮሉበት ቅጣት ውሳኔ እኔ ዘንድ አይደለም። ፍርዱ በአላህ ብቻ ነው። አላህ እውነቱን ይፈርዳል። እርሱም ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነውና በላቸው። ያ የምትቻኮሉበት ቅጣት እኔ ዘንድ በሆነ ኖሮ በእኔና በእናንተ መካከል ነገሩ ቅጣታችሁ በተፈፀመ ነበር። አላህ በደለኞችን አዋቂ ነው በላቸው።

۞ وَعِندَهُۥ مَفَاتِحُ ٱلۡغَيۡبِ لَا يَعۡلَمُهَآ إِلَّا هُوَۚ وَيَعۡلَمُ مَا فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۚ وَمَا تَسۡقُطُ مِن وَرَقَةٍ إِلَّا يَعۡلَمُهَا وَلَا حَبَّةٖ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡأَرۡضِ وَلَا رَطۡبٖ وَلَا يَابِسٍ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ﴿٥٩﴾ وَهُوَ ٱلَّذِي يَتَوَفَّىٰكُم بِٱلَّيۡلِ وَيَعۡلَمُ مَا جَرَحۡتُم بِٱلنَّهَارِ ثُمَّ يَبۡعَثُكُمۡ فِيهِ لِيُقۡضَىٰٓ أَجَلٞ مُّسَمّٗىۖ ثُمَّ إِلَيۡهِ مَرۡجِعُكُمۡ ثُمَّ يُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٦٠﴾

**59-60.** የሩቅ ሚስጥሮች መክፈቻዎች ሁሉ እርሱ ዘንድ ብቻ ናቸው። ከእርሱ በስተቀር ማንም አያውቃቸውም። በየብስና በባህር ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል። አንዲትም ቅጠል አትረግፍም አላህ የሚያውቃት ብትሆን እንጂ። በመሬት ጨለማዎች ውስጥ ቅንጣት እርጥብም ሆነ ደረቅ አንድም ነገር የለም ግልፅ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበ ቢሆን እንጂ። እርሱ (አላህ) ያ፣ በሌሊት የሚያስተኛችሁ በቀን የሰራችሁትን ሁሉ የሚያውቅ ከዚያም የተወሰነው ጊዜ ይፈፀም ዘንድ በቀን ውስጥ የሚቀሰቅሳችሁ ነው። ከዚያም መመለሻችሁ ወደ እርሱ ብቻ ነው። ከዚያም ትሰሩት የነበራችሁትን ነገር ሁሉ አንድ በአንድ ይነግራችኋል።

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (53-59) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በኢስላም ውስጥ ትልቅነት በዘር፤ በገንዘብ፤ በስልጣን፤ በግርማ ሞገስ ሳይሆን በእምነትና በመልካም ስራ መሆኑን፤
2. ምን እንደሚያስከትልበት ሳያውቅ መጥፎ ስራ የሰራ ሰው ተፀፅቶ ወደ አላህ ተውበት ቢያደርግ አላህ ይቅር ባይ መሆኑን፤
3. አላህ ሁሉን ነገር የሚያውቅ መሆኑን፤
4. ነብዩ የአላህ ባሪያ እንጂ «ስውር ነገሮችን አውቃለሁ ከአላህ ካዝና የፈለኩትን ማድረግ እችላለሁ» ብለው እንደማያውቁ እንማራለን።

وَهُوَ ٱلْقَاهِرُ فَوْقَ عِبَادِهِۦ ۖ وَيُرْسِلُ عَلَيْكُمْ حَفَظَةً حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَ أَحَدَكُمُ ٱلْمَوْتُ
تَوَفَّتْهُ رُسُلُنَا وَهُمْ لَا يُفَرِّطُونَ ﴿٦١﴾ ثُمَّ رُدُّوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ مَوْلَىٰهُمُ ٱلْحَقِّ ۚ
أَلَا لَهُ ٱلْحُكْمُ وَهُوَ أَسْرَعُ ٱلْحَـٰسِبِينَ ﴿٦٢﴾

**61-62.** እርሱም ከባሮቹ በላይ ሲሆን ሁሉን አሸናፊ ነው። በእናንተ ላይም✳ ተጠባባቂዎች መላዕክትን ይልካል። አንዳችሁንም የሞት ሰዓቱ በመጣበት ጊዜ (የሞት) መልዕክተኞቻችን ትዕዛዛትን የማያጓድሉ ሲሆኑ ይገድሉታል። ከዚያም እውነተኛ ወደ ሆነው ጌታቸው ወደ አላህ ይመለሳሉ። (ሙስሊሞች ሆይ!) ንቁ፣ አዋጅ ፍርዱ ለእርሱ ብቻ ነው። እርሱም ከተቆጣጣሪዎች ሁሉ ይበልጥ ፈጣን ነው።

✳ (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ስለ አላህ ሲናሩ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ በናንተ ላይ የተመረጡትን መላዕክት የሰራችሁትን መልካምም ሆነ መጥፎ ተግባራት እንዲፅፍ አዟል። እንዴት እንደሚፅፍም አመልክቷቸዋል። አንድ ሰው መልካም ተግባራትን ለመፈፀም ተነሳስቶ ባይፈፅማቸው አላህ የመልካም ተግባራትን ሙሉ ምንዳ ይፅፍለታል። መልካም ተግባራትን ለመፈፀም ተነሳስቶ ቢፈፅማቸው አላህ ለዚህ ሰው መልካም ስራ መፈፀም ከአስር እስከ ሰባት መቶ ከዚያም እጥፍ የሚደርስ ምንዳ ይፅፍለታል። አንድ ሰው መጥፎ ተግባር ለመፈፀም ተነሳስቶ ባይፈፅመው አላህ የመልካም ተግባር ምንዳ ይፅፍለታል። አንድ ሰው መጥፎ ተግባርን ለመፈፀም ተነሳስቶ ቢፈፅመው አላህ የአንዲትን መጥፎ ተግባር ምንዳ ይፅፍለታል።»

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በቀንና በሌሊት እየተለዋወጡ ወደእናንተ የሚመጡ መላዕክት አሉ። ሁሉም መላዕክት በፈጅርና በዐስር ሶላት ወቅቶች ይገናኛሉ። ሌሊቱን ሙሉ ከእናንተ ጋር የነበሩት መላዕክት ወደ አላህ ሲመለሱ አላህ እንዲህ ሲል ይጠይቃቸዋል። ነገር ግን እሱ ምላሻቸውን ከነርሱ በበለጠ ያውቀዋል። «ባሪያዎቼን በምን ሁኔታ ላይ ተዋቿኋቸው?» እነርሱም «ወደነርሱ ስንመጣ እየሰገዱ ነበር። አሁንም ትተናቸው ስንመጣ እየሰገዱ ነበር» በማለት ይመልሳሉ። «ከናንተ መካከል አንዱ የፋቲሐህን አንብቦ ከጨረሰ በኋላ «አሚን» ካለ በሰማይ ላይ የሚገኙት መላዕክትም እንዲሁ «አሚን» ይላሉ። የሁለቱ የሰውዬውና የመላዕክት አሚን ማለት ከተገናኙ፤ የሰውዬው የቀድሞ ኃጢአቶች በሙሉ ይሰረዙለታል።»

قُلْ مَن يُنَجِّيكُم مِّن ظُلُمَـٰتِ ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ تَدْعُونَهُۥ تَضَرُّعًا وَخُفْيَةً لَّئِنْ أَنجَىٰنَا مِنْ هَـٰذِهِۦ
لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّـٰكِرِينَ ﴿٦٣﴾ قُلِ ٱللَّهُ يُنَجِّيكُم مِّنْهَا وَمِن كُلِّ كَرْبٍ ثُمَّ أَنتُمْ تُشْرِكُونَ ﴿٦٤﴾

**63-64.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያ ከየብስና ከባህር ጨለማዎች በግልፅና በሚስጢር የምትጠሩት ስትሆኑ ከእነዚህ ቢያድነን ከአመስጋኞች እንሆናለን ስትሉ የሚያድናችሁ ማንነው? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከእሷና ከጭንቅም ሁሉ ያድናችኋል። ከዚያ እናንተ በእሱ በዐድ አምልኮን ታጋራላችሁ በላቸው።

قُلْ هُوَ ٱلْقَادِرُ عَلَىٰٓ أَن يَبْعَثَ عَلَيْكُمْ عَذَابًا مِّن فَوْقِكُمْ أَوْ مِن تَحْتِ أَرْجُلِكُمْ أَوْ يَلْبِسَكُمْ
شِيَعًا وَيُذِيقَ بَعْضَكُم بَأْسَ بَعْضٍ ۗ ٱنظُرْ كَيْفَ نُصَرِّفُ ٱلْـَٔايَـٰتِ لَعَلَّهُمْ يَفْقَهُونَ ﴿٦٥﴾ وَكَذَّبَ بِهِۦ
قَوْمُكَ وَهُوَ ٱلْحَقُّ ۚ قُل لَّسْتُ عَلَيْكُم بِوَكِيلٍ ﴿٦٦﴾ لِّكُلِّ نَبَإٍ مُّسْتَقَرٌّ ۚ وَسَوْفَ تَعْلَمُونَ ﴿٦٧﴾

**65-67.** እርሱ (አላህ) ከበላያችሁ ወይም ከእግሮቻችሁ በታች ቅጣትን በእናንተ ላይ ሊልክ ወይም የተለያዩ ሕዝቦች ስትሆኑ ሊያደባልቃችሁና ከፊላችሁን የከፊሉን ጭካኔ ሊያቀምስ ቻይ ነው በላቸው። ያውቁ ዘንድ አንቀፆችን እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት። በእርሱም (ቁርአን ከአላህ የመጣ) እውነት ሲሆን ህዝቦችህ ግን እሱን አስተባበሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በናንተ ላይ ጠባቂ አይደለሁም በላቸው። ለየትንቢቱ ሁሉ የሚደርስበት መፈፀሚያ ጊዜ አለው። ወደ ፊትም በትክክል ታዩታላችሁ።

ከቤት እንስሳዎች ምዕራፍ (65) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዚህ አንቀፅ መጀመሪያ ላይ ያሉት መልዕክቶች ሲወርዱ ነብዩ (ﷺ) «ከእኔ በኋላ በሰይፍ አንገት ለአንገት የሚቃለሉ ከሓዲያን እንዳትሆኑ» በማለት ሲነግራቸው «በአላህ ብቸኛ አምላክነት እንመስክራለን በእርስዎ መልዕክተኛነትም እንዲሁ» አሉና አንዳንዶች ይህ ፍፁም አይደረግም ሲሉ ነበር የዚህ አንቀፅ መዝጊያ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَإِذَا رَأَيْتَ ٱلَّذِينَ يَخُوضُونَ فِىٓ ءَايَـٰتِنَا فَأَعْرِضْ عَنْهُمْ حَتَّىٰ يَخُوضُوا۟ فِى حَدِيثٍ غَيْرِهِۦ ۚ
وَإِمَّا يُنسِيَنَّكَ ٱلشَّيْطَـٰنُ فَلَا تَقْعُدْ بَعْدَ ٱلذِّكْرَىٰ مَعَ ٱلْقَوْمِ ٱلظَّـٰلِمِينَ ﴿٦٨﴾ وَمَا عَلَى ٱلَّذِينَ
يَتَّقُونَ مِنْ حِسَابِهِم مِّن شَىْءٍ وَلَـٰكِن ذِكْرَىٰ لَعَلَّهُمْ يَتَّقُونَ ﴿٦٩﴾

**68-69.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ አንቀፆቻችንን ለማስተባበል ወደ ክርክር የሚገቡትን ሰዎች በምታይ ጊዜ በሌላ ወሬ እስከሚገቡ ድረስ ተዋቸው። ሰይጣንም (መከልከልህን) ቢያስረሳህና አብረሀቸው ሆነህ እንኳን ካስታወስክ በኋላ ከበደለኞች ሕዝቦች ጋር አትቀመጥ። በእነዚያም በሚጠነቀቁት ህዝቦች ላይ በሂሳባቸው ምንም የለባቸውም። ግን ይጠነቀቁ ዘንድ መገሰጽ አለባቸው።

وَذَرِ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ دِينَهُمْ لَعِبًا وَلَهْوًا وَغَرَّتْهُمُ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا ۚ وَذَكِّرْ بِهِۦٓ أَن تُبْسَلَ نَفْسٌۢ بِمَا
كَسَبَتْ لَيْسَ لَهَا مِن دُونِ ٱللَّهِ وَلِىٌّ وَلَا شَفِيعٌ وَإِن تَعْدِلْ كُلَّ عَدْلٍ لَّا يُؤْخَذْ مِنْهَآ ۗ أُو۟لَـٰٓئِكَ
ٱلَّذِينَ أُبْسِلُوا۟ بِمَا كَسَبُوا۟ ۖ لَهُمْ شَرَابٌ مِّنْ حَمِيمٍ وَعَذَابٌ أَلِيمٌۢ بِمَا كَانُوا۟ يَكْفُرُونَ ﴿٧٠﴾

**70.** እነዚያንም ሃይማኖታቸውን ጨዋታና ቀልድ አድርገው የያዙትንና ቅርቢቱ ሕይወት ያታለለቻቸውን ሰዎች ተዋቸው። በእርሱም (በቁርኣን) ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ እንዳትጠፋ አስታውስ። ለእርሷ ከአላህ ሌላ ወዳጅም ሆነ አማላጅ ማንም የላትም። ፊዳ የተባለን ሁሉ ብትከፍል እንኳን ተቀባይነት የላትም። እነዚህ እነዚያ በሰሩት ስራ የተጠፉት ናቸው። በክህደታቸው ምክንያት ከፈላ ውሃ መጠጥና አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

قُلْ أَنَدْعُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُنَا وَلَا يَضُرُّنَا وَنُرَدُّ عَلَىٰٓ أَعْقَابِنَا بَعْدَ إِذْ هَدَىٰنَا ٱللَّهُ
كَٱلَّذِى ٱسْتَهْوَتْهُ ٱلشَّيَـٰطِينُ فِى ٱلْأَرْضِ حَيْرَانَ لَهُۥٓ أَصْحَـٰبٌ يَدْعُونَهُۥٓ إِلَى ٱلْهُدَى ٱئْتِنَا ۗ قُلْ إِنَّ
هُدَى ٱللَّهِ هُوَ ٱلْهُدَىٰ ۖ وَأُمِرْنَا لِنُسْلِمَ لِرَبِّ ٱلْعَـٰلَمِينَ ﴿٧١﴾ وَأَنْ أَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَٱتَّقُوهُ ۚ وَهُوَ ٱلَّذِىٓ
إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ﴿٧٢﴾ وَهُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ بِٱلْحَقِّ ۖ وَيَوْمَ يَقُولُ كُن فَيَكُونُ ۚ قَوْلُهُ
ٱلْحَقُّ ۚ وَلَهُ ٱلْمُلْكُ يَوْمَ يُنفَخُ فِى ٱلصُّورِ ۚ عَـٰلِمُ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَـٰدَةِ ۚ وَهُوَ ٱلْحَكِيمُ ٱلْخَبِيرُ ﴿٧٣﴾

**71-73.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአላህ ሌላ የማይጠቅምንና የማይጎዳን እንገዛለን? አላህ በቀናው መንገድ ከመራን በኋላ የኋሊት እንመለሳለን? እንደዚያ በምድር ላይ የዋለለ ሲሆን ሰይጣናት እንዳሳሳቱንና ለእርሱ ወደ እኛ ና እያሉ ወደ ቅን መንገድ የሚጠሩ ወዳጆች እንዳሉትና (እንደማይከተላቸው) ሰው እንሆናለን? በላቸው። የአላህ መንገድ ቀጥተኛው መንገድ ነው። ለዓለማት ጌታ ልንገዛም ታዘዝን በላቸው። ሶላትን በትክክል ስገዱ አላህን ፍሩትም። እርሱም ያ ወደርሱ የምትሰበሰቡበት አምላክ ነው ተብለንም ታዘናል በላቸው። እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በትክክል የፈጠረ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁን የሚልበትንና ወዲያውም የሚሆንበትን ቀን (አስታውስ)። ቃሉ እውነት ነው። በቀንዱ በሚነፋበት ቀን ንግስናው የርሱ ብቻ ነው። ሩቁንና ቅርቡን አዋቂ ነው። እርሱም ጥበበኛና ውስጠ አዋቂ ነው።

### ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (60-73) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. እንቅልፍ ትንሹ ሞት እንደሆነና ከእንቅልፍ መንቃት ከሞት መቀስቀስ የሚችለው አላህ ለመኖሩ ግልፅ ማስረጃ መሆኑን፤
2. አላህ የሰውን ልጅን የሚጠብቁና አንደበቱንም ተግባሩንም የሚመዘግቡ፤ ሩሁንም ከአካሉ የሚያወጡ መላኢኮች እንዳሉት፤
3. ሰዎች በችገራቸው ጊዜ ወደ አላህ መጠጋታቸው፤
4. በአላህ ብቸኝነት ማመን የሰው ልጆች የተፈጥሮ እምነታቸው መሆኑን፤

5. በአላህ ቃል ከሚያፌዙ እና በዲን ከሚያስተባብሉ አካሎች ጋር መቀራረብ፤ አብሮ ማሳለፍ ጓደኝነት መያዝ ተገቢ እንዳልሆነ፤
6. ትክክለኛ አማኝ በዲን የሚያፌዙ ሰዎችን መምከር እንጂ በምንም መልኩ መሳተፍ እንደሌለበት፤
7. ቁርኣን ከመካሪዎች ሁሉ የበለጠ በመሆኑ ሰዎችን የሚመክሩና የሚያስተምሩ ሰዎች የሱን ፈለግና ጥበብ መከተል እንደሚገባቸው፤
8. የጣኦት አምላኪዎችና የአላህ አምላኪዎች ምሳሌያቸው ምን እንደሆነ እንማራለን።

۞ وَإِذْ قَالَ إِبْرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ ءَازَرَ أَتَتَّخِذُ أَصْنَامًا ءَالِهَةً إِنِّيٓ أَرَىٰكَ وَقَوْمَكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ﴿٧٤﴾

**74.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂም ለአባቱ ለአዘር፡- ‹ጣኦትን አማልክት አድርገህ ትይዛለህን? እኔ አንተንም ወገኖችህንም ግልጽ ጥመት* ውስጥ ሆናችሁ አየኋችሁ ባለው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የትንሳኤ ቀን ኢብራሂም አባቱን አዘርን ፊቱ ጠቁሮና አቧራ ለብሶ ያገኘዋል። አባቱም «ዛሬ ትዕዛዝህን እምቢ አልልም» ይለዋል። ኢብራሂምም «ጌታዬ ሆይ! ሰዎች ከቀብራቸው በሚቀሰቀሱበት ወቅት ላታዋርደኝ ቃል ገብተህልኝ ነበር። አባቴን ከማዋረድ የበለጠ ምን አይነት ውርደት ይኖርህ ይሆን?» በማለት አላህን ይጠይቃል። አላህም «እኔ በእርግጥ ጀነትን በከሓዲያን ላይ እርም አድርጌያለሁ» ይላል። ከዚያም ለኢብራሂም «ከእግርህ ስር ያለው ነገር ምንድ ነው?»ይባላል። እሱም ወደ እግሩ ሲመለከት የታረደ እንሰሳ ተለጥፎበት ይመለከታል። ይህም እንሰሳ ተወስዶ ወደ ጀሀነም ይወረወራል።»

وَكَذَٰلِكَ نُرِيٓ إِبْرَٰهِيمَ مَلَكُوتَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَلِيَكُونَ مِنَ ٱلْمُوقِنِينَ ﴿٧٥﴾ فَلَمَّا جَنَّ عَلَيْهِ
ٱلَّيْلُ رَءَا كَوْكَبًاۖ قَالَ هَٰذَا رَبِّيۖ فَلَمَّآ أَفَلَ قَالَ لَآ أُحِبُّ ٱلْءَافِلِينَ ﴿٧٦﴾ فَلَمَّا رَءَا ٱلْقَمَرَ بَازِغًا
قَالَ هَٰذَا رَبِّيۖ فَلَمَّآ أَفَلَ قَالَ لَئِن لَّمْ يَهْدِنِي رَبِّي لَأَكُونَنَّ مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلضَّآلِّينَ ﴿٧٧﴾ فَلَمَّا رَءَا
ٱلشَّمْسَ بَازِغَةً قَالَ هَٰذَا رَبِّي هَٰذَآ أَكْبَرُۖ فَلَمَّآ أَفَلَتْ قَالَ يَٰقَوْمِ إِنِّي بَرِيٓءٞ مِّمَّا تُشْرِكُونَ ﴿٧٨﴾
إِنِّي وَجَّهْتُ وَجْهِيَ لِلَّذِي فَطَرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ حَنِيفًاۖ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿٧٩﴾

**75-79.** ልክ በዚህ አኳኋን ኢብራሂም ጽኑ እምነት ይኖረው ዘንድ የሰማያትንና የምድርን ግዛት አሳየነው። ሌሊቱ በጽልመቱ በሸፈነው ጊዜ አንድ ኮከብ አየ። «ይህ ጌታዬ ነው» አለም። ኮከቡ በጠለቀ ጊዜም፡- ጠላቂዎችን አልወድም። አለ። ጨረቃውን ደምቆ ባየ ጊዜ፡- «ይህ ጌታዬ ነው» አለ። ጨረቃው በጠለቀ ጊዜ፡- ጌታዬ ቅኑን ጎዳና ካልመራኝ መንገድ ከተሳሳቱ ሰዎች እሆናለሁ አለ። ፀሐይዋንም ደምቃ ባየ ጊዜ፡- «ይህ ጌታዬ ነው።» ይህ በጣም ትልቅ ነው አለ። በጠለቀችም ጊዜ፡- ‹ወገኖቼ ሆይ፣ እኔ ከምታጋሩት ሁሉ የጠራሁ ነኝ አለ› እኔ ቀጥተኛው ስሆን ፊቴን ሰማያትንና ምድርን ወደ ፈጠረው አምላክ አላህ አዙሬያለሁ። እኔም ከአጋሪዎችም አይደለሁም (አለ)።

وَحَآجَّهُۥ قَوۡمُهُۥۚ قَالَ أَتُحَٰٓجُّوٓنِّي فِي ٱللَّهِ وَقَدۡ هَدَىٰنِۚ وَلَآ أَخَافُ مَا تُشۡرِكُونَ بِهِۦٓ إِلَّآ أَن يَشَآءَ
رَبِّي شَيۡـٔٗاۚ وَسِعَ رَبِّي كُلَّ شَيۡءٍ عِلۡمًاۚ أَفَلَا تَتَذَكَّرُونَ ﴿٨٠﴾ وَكَيۡفَ أَخَافُ مَآ أَشۡرَكۡتُمۡ وَلَا تَخَافُونَ
أَنَّكُمۡ أَشۡرَكۡتُم بِٱللَّهِ مَا لَمۡ يُنَزِّلۡ بِهِۦ عَلَيۡكُمۡ سُلۡطَٰنٗاۚ فَأَيُّ ٱلۡفَرِيقَيۡنِ أَحَقُّ بِٱلۡأَمۡنِۖ إِن كُنتُمۡ
تَعۡلَمُونَ ﴿٨١﴾ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَلَمۡ يَلۡبِسُوٓاْ إِيمَٰنَهُم بِظُلۡمٍ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلۡأَمۡنُ وَهُم مُّهۡتَدُونَ ﴿٨٢﴾
وَتِلۡكَ حُجَّتُنَآ ءَاتَيۡنَٰهَآ إِبۡرَٰهِيمَ عَلَىٰ قَوۡمِهِۦۚ نَرۡفَعُ دَرَجَٰتٖ مَّن نَّشَآءُۗ إِنَّ رَبَّكَ حَكِيمٌ عَلِيمٞ ﴿٨٣﴾

**80-83.** ወገኖቹም ተከራከሩት በአላህ አንድነት በእርግጥ የመራኝ ሲሆን ትከራከሩኛላችሁን? በእርሱም የምታጋሩትን ነገር አልፈራም። ግን ጌታ ቢሻ ያገኘኛል። ጌታዬም በሁሉ ነገር እውቀቱ ሰፊ መሆኑን አትገነዘቡምን አላቸው። በእናንተ ላይ በእርሱ ማስረጃ ያላወረደበትን እናንተ ማጋራታችሁን የማትፈሩ ስትሆኑ የምታጋሩትን ጣዖት እንዴት እኔ እፈራለሁ!። የምታውቁም ብትሆኑ ከሁለቱ ክፍሎች በፀጥታ ይበልጥ ተገቢው ማንኛው ነው? አለ። እነዚያ በአላህ ያመኑና እምነታቸውን በእሱ በማጋራት ያልቀላቀሉ ሰዎች ሁሉ እነዚያ ለእነርሱ የተሟላ ፀጥታ አለላቸው። ወደ ቀናው መንገድ የተመሩም እነርሱው ብቻ ናቸው። እነዚህ ማስረጃዎቻችን ናቸው። ለኢብራሂም በህዝቦቹ ላይ አስረጅ እንዲሆኑ ሰጠነው። የምንፈልገውን ሰው በደረጃዎች ከፍ እናደርጋለን። ጌታህ ጥበበኛና አዋቂ ነውና።

ከቤት እንስሳዎች ምዕራፍ (82) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- አንድ ከሐዲ ሙስሊሞች ወዳሉበት በመግባት ሶስት ሙስሊሞችን በተከታታይ ከገደለ በኋላ ይፀፀታል። እናም «ኢስላም ይጠቅመኛልን» ብሎ ይጠይቃል። ነብዩ (ﷺ) «አዎ» ብለው መልስ በመስጠታቸው ፈረሱን ቀስቅሶ በካፊሮች ላይ በመዝመት ሁለት ሰዎችን ከገደለ በኋላ ጠላት ስለገደለው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ እና ሱዩጢ)

وَوَهَبۡنَا لَهُۥٓ إِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَۚ كُلًّا هَدَيۡنَاۚ وَنُوحًا هَدَيۡنَا مِن قَبۡلُۖ وَمِن ذُرِّيَّتِهِۦ دَاوُۥدَ
وَسُلَيۡمَٰنَ وَأَيُّوبَ وَيُوسُفَ وَمُوسَىٰ وَهَٰرُونَۚ وَكَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٨٤﴾ وَزَكَرِيَّا وَيَحۡيَىٰ
وَعِيسَىٰ وَإِلۡيَاسَۖ كُلّٞ مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٨٥﴾ وَإِسۡمَٰعِيلَ وَٱلۡيَسَعَ وَيُونُسَ وَلُوطٗاۚ وَكُلّٗا فَضَّلۡنَا عَلَى
ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٨٦﴾ وَمِنۡ ءَابَآئِهِمۡ وَذُرِّيَّٰتِهِمۡ وَإِخۡوَٰنِهِمۡۖ وَٱجۡتَبَيۡنَٰهُمۡ وَهَدَيۡنَٰهُمۡ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ﴿٨٧﴾

**84-87.** ለእርሱም ነብዩ ኢስሀቅንና የልጅ ልጁን ነብዩ ያዕቁብንም ሰጠነው። ሁሉንም ወደቀናው መንገድ መራናቸው። ኑህንም ከእነርሱ በፊት ወደ ቀናው መንገድ መራነው። ከዘሮቹም ነብዩ ዳውድን፤ ነብዩ ሱለይማንን፤ ነብዩ አዩብንም፤ ነብዩ ዩሱፍን፤ ነብዩ ሙሳንና፤ ነብዩ ሀሩንንም (መራን)። ልክ እንደዚሁ በጎ ሰሪዎችን እንመነዳለን። ነብዩ ዘከርያንም፣ ነብዩ ያሕያንም፣ ነብዩ

ዒሳንም፣ ነብዩ ኢልያስንም ወደ ቀናው መንገድ መራን። ሁሉም ከመልካሞች ናቸው። ነብዩ ኢስማኢልንም፣ ነብዩ አል የሰዕንም፣ ነብዩ ዩኑስንም፣ ነብዩ ሉጥንም መራን። ሁሉንም በዓለማት ላይ አበለጥናቸው። ከአባቶቻቸውም ከዘሮቻቸውም፤ ከወንድሞቻቸውም ብዙ ሰዎችን (መራን)። መረጥናቸውም። ወደ ቀጥታውም መንገድ መራናቸው።

ذَٰلِكَ هُدَى ٱللَّهِ يَهْدِى بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ ۚ وَلَوْ أَشْرَكُوا۟ لَحَبِطَ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟
يَعْمَلُونَ ﴿٨٨﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ءَاتَيْنَٰهُمُ ٱلْكِتَٰبَ وَٱلْحُكْمَ وَٱلنُّبُوَّةَ ۚ فَإِن يَكْفُرْ بِهَا هَٰٓؤُلَآءِ
فَقَدْ وَكَّلْنَا بِهَا قَوْمًا لَّيْسُوا۟ بِهَا بِكَٰفِرِينَ ﴿٨٩﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ هَدَى ٱللَّهُ ۖ فَبِهُدَىٰهُمُ ٱقْتَدِهْ ۗ قُل
لَّآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا ۖ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرَىٰ لِلْعَٰلَمِينَ ﴿٩٠﴾

**88-90.** ይህ የአላህ መመሪያ ነው። በእርሱ ከባሮቹ የሚሻውን ሰው ወደ ቀናው መንገድ ይመራል። በአላህ ባጋሩም ኖሮ ይሰሩት የነበሩት መልካም ተግባር ሁሉ ለእነርሱ በታበሰባቸው ነበር። እነዚህ እነዚያ መጽሐፍትንና ጥበብን ነብይነትንም የሰጠናቸው ሰዎች ናቸው። የመካ ከሐዲያን በእርሷ ቢክዱ በእርሷ የማይክዱ ሕዝቦች አዘጋጅተንላታል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ እነዚያ ነብያት አላህ የመራቸው ናቸው። ስለሆነም ፈለጋቸውን ተከተል። ቁርኣንን ለማስተማር ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም። እርሱ ለዓለማት ግሳጼ ሊሆን የወረደ እንጂ ሌላ አይደለም በላቸው።

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (74-90) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በጠቅላላ የነብያት ታሪክም ሆነ በነብዩ ኢብራሂም ታሪክ ብዙ አስተምህሮት ያላቸው በመሆኑ ሁሉም ሙስሊም ሊረዳቸው እንደሚገባ፤
2. በእምነት የሚከራከር ሰው መከራከር ያለበት ግልፅ መረጃዎችን በማቅረብ እንጂ በመሳደብ፤ በመገላመጥ ሀይለ ቃል በመጠቀም መከራከራ እንደሌለበት፤
3. እውነትን አጥብቆ በመያዝ የውሸቱ ደጋፊዎች የቱንም ያህል ጉልበት ቢኖራቸውም እጅ አለመስጠት፤
4. በሁለቱም ዓለም ሰላም የሚገባቸው በአላህ በትክክል የሚያምኑ ክፍሎች ብቻ እንደሆኑ፤
5. ትክክለኛ እምነትን መያዝና በዳይ አለመሆን ውስጣዊም ሆነ ውጫዊ ሰላም ለማግኘት ዋስትና መሆናቸውን፤
6. በአላህ ማጋራት የበደሎች ሁሉ በደል መሆኑን፤
7. የአላህ ነብያትና መልዕክተኞች የምርጦች ሁሉ ምርጥ እንደሆኑ እንደሆኑና እነሱን መከተል እንዳለብን እንማራለን።

وَمَا قَدَرُواْ ٱللَّهَ حَقَّ قَدۡرِهِۦٓ إِذۡ قَالُواْ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ عَلَىٰ بَشَرٖ مِّن شَيۡءٖۗ قُلۡ مَنۡ أَنزَلَ ٱلۡكِتَٰبَ
ٱلَّذِي جَآءَ بِهِۦ مُوسَىٰ نُورٗا وَهُدٗى لِّلنَّاسِۖ تَجۡعَلُونَهُۥ قَرَاطِيسَ تُبۡدُونَهَا وَتُخۡفُونَ كَثِيرٗاۖ
وَعُلِّمۡتُم مَّا لَمۡ تَعۡلَمُوٓاْ أَنتُمۡ وَلَآ ءَابَآؤُكُمۡۖ قُلِ ٱللَّهُۖ ثُمَّ ذَرۡهُمۡ فِي خَوۡضِهِمۡ يَلۡعَبُونَ ٩١

**91.** አላህ በሰው ላይ ምንም አላወረደም ባሉ ጊዜ አላህን ተገቢውን ክብሩን አላከበሩትም። እንዲህ በላቸው ያንን ለሰዎች ብርሃንና ቅን መመሪያ ሆኖ ሙሳ ያመጣውን መጽሐፍ ክፍልፍሎች የምታደርጉት ስትሆኑ ማን አወረደው? የወደዳችሁትንም ብዙውንም ትደብቃላችሁ። ብዙውን ይፋ ታደርጋላችሁ። እናንተም ሆናችሁ አባቶቻችሁም ያላወቃችሁትን ተስተማራችሁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ አወረደው በላቸው። ከዚያ በውሸታቸው ውስጥ የሚጫወቱ ሲሆኑ ተዋቸው።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (91) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ማሊክ ቢን ሰይፍ የተባለ አንድ አይሁድ ከነብዩ (ﷺ) ጋር ሲከራከር መጥቶ ሳለ ነብዩ (ﷺ) «ተውራትን በሙሳ ላይ ባወረደው ጌታ አላህ ይሁንብህና አላህ ወፈፍራም ዐሊሞች ን ይጠላል የሚል ጥቅስ በተውራት ላይ አላየህምን?» አሉት። እነርሱም በጣም ወፍራም ነበርና በዚህ ነብዩ (ﷺ) ንግግር ተቆጣና ተውራትን በማስተባበል «አላህ በግለሰቦች ላይ ምንም ያወረደውና ያለው ነገር የለም» ሲል የውሸት ምላሽ ሰጠ። አብረውት የነበሩት ሰዎች ደግሞ በንግግሩ ሀሰትነት በመገረም ተውራትን ስለሚያውቁ «ወየውልህ አላህ በነብዩ ሙሳ ላይ እንኳን ምንም አላወረደምን?» በማለት ሲከእሱት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَهَٰذَا كِتَٰبٌ أَنزَلۡنَٰهُ مُبَارَكٞ مُّصَدِّقُ ٱلَّذِي بَيۡنَ يَدَيۡهِ وَلِتُنذِرَ أُمَّ ٱلۡقُرَىٰ وَمَنۡ حَوۡلَهَاۚ
وَٱلَّذِينَ يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِ يُؤۡمِنُونَ بِهِۦۖ وَهُمۡ عَلَىٰ صَلَاتِهِمۡ يُحَافِظُونَ ٩٢

**92.** ይህ ያወረድነው ብሩክና ያንንም በፊት የነበረውን መጽሐፍ አረጋጋጭ ነው። የከተሞችንም እናት መካንና በዙሪያቸው ያሉትንም ሰዎች ልታስጠነቅቅበት አወረድነው። እነዚያም በመጨረሻይቱ ዓለም የሚያምኑት ሰዎች እነርሱ በሶላታቸው የሚጠባበቁ ሲሆኑ በእርሱ ያምናሉ።

وَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّنِ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوۡ قَالَ أُوحِيَ إِلَيَّ وَلَمۡ يُوحَ إِلَيۡهِ شَيۡءٞ وَمَن قَالَ
سَأُنزِلُ مِثۡلَ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُۗ وَلَوۡ تَرَىٰٓ إِذِ ٱلظَّٰلِمُونَ فِي غَمَرَٰتِ ٱلۡمَوۡتِ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ بَاسِطُوٓاْ
أَيۡدِيهِمۡ أَخۡرِجُوٓاْ أَنفُسَكُمُۖ ٱلۡيَوۡمَ تُجۡزَوۡنَ عَذَابَ ٱلۡهُونِ بِمَا كُنتُمۡ تَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ غَيۡرَ
ٱلۡحَقِّ وَكُنتُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِهِۦ تَسۡتَكۡبِرُونَ ٩٣ وَلَقَدۡ جِئۡتُمُونَا فُرَٰدَىٰ كَمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ أَوَّلَ

مَرَّةٍ وَتَرَكْتُم مَّا خَوَّلْنَٰكُمْ وَرَآءَ ظُهُورِكُمْ ۖ وَمَا نَرَىٰ مَعَكُمْ شُفَعَآءَكُمُ ٱلَّذِينَ زَعَمْتُمْ أَنَّهُمْ فِيكُمْ شُرَكَٰٓؤُا۟ ۚ لَقَد تَّقَطَّعَ بَيْنَكُمْ وَضَلَّ عَنكُم مَّا كُنتُمْ تَزْعُمُونَ ﴿٩٤﴾

**93-94.** በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ወይም ወደ እርሱ ምንም ያልተወረደለት ሲሆን ወደ እኔ ተወረደልኝ ካለና አላህ ያወረደውን አይነት በእርግጥ ማውረድ እችላለሁ ካለ ሰው ይበልጥ እራሱን በዳይ ማን ነው፣ በደለኞችን በሞት መከራዎች ውስጥ በሆኑ ጊዜ መላዕክት እጆቻቸውን ዘርጊዎች ሆነው (ለቅጥጥብ) ለመሳለቅ ነፍሶቻችሁን አውጡ። ከአላህ ላይ እውነትን ያልሆነን ነገር ትናገሩም የነበራችሁና በአንቀፆችም ላይ ትኮሩ በነበራችሁት ምክንያት ዛሬ የውርደት ቅጣት* ትመነዳላችሁ በሚሏቸው ጊዜ ብታይ ኖሮ። (አስደንጋጭ ነገር ባየህ ነበር)። በመጀመሪያ ጊዜ እንደፈጠርናችሁ ሆናችሁ የሰጠናችሁን ሀብት ሁሉ ከጀርባዎቻችሁ ኋላ የተዋችሁ ስትሆኑ ለየብቻችሁ ሆናችሁ በእርግጥ ወደ እኛ መጣችሁ። እነዚያንም እነርሱ በእናንተ ውስጥ ለአላህ ተጋሪዎቹ ናቸው። የምትሏቸውን አማላጆቻችሁን ከናንተ ጋር አናይም። ግንኙነታችሁ በእርግጥ ተቋረጠ። ከናንተም ያ ያማልደናል የምትሉት ጠፋ ይባላሉ።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ አማኝ የሆነ ሰው ቀብር ውስጥ ከተረጋጋ በኋላ «ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም። ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው» ብሎ ይመሰክራል። ይህም «ከአላህ እነዚያን ያመኑትን በቅርቢቱም ሕይወት በመጨረሻይቱም በተረጋገጠው ቃል ላይ ያረጋቸዋል» የሚለው የአላህ ቃሉ ነው።»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ ባሪያ ቀብር ውስጥ ከተደላደለና ጓደኞቹ ቀብረውት ከተመለሱም በኋላ የኮቴያቸውን ድምፅ ይሰማል። ከዚያም ሁለት መላዕክት እንዲቀመጥ ካደረጉት በኋላ «ስለዚህ ሰው ስለ ሙሐመድ ምን ነበር የምትል?» ሲሉ ይጠይቁታል። እሱም «እሱ የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ መሆኑን እመሰክራለሁ» ይላል። መላዕክቱም በእሳት ውስጥ ያለህን መቀመጫ ተመልከት። አላህ ይህን መቀመጫህን በጀነት መቀመጫ ለውጦልሃል» ይሉታል። ከሃዲ ወይም መናፍቅ የሆነው ግን«ምንም አላውቅም። ሰዎች የሚሉትን እናገር ነበር»ይላል። «አላወቅክምም አላነበብክምም» ይባላል። ከዚያ በብረት መዶሻ ከሁለቱ ጆሮዎቹ ላይ ይመታል። በጣምም ይጮኃል፤ ድምፁም ከሰው ልጆችና ከአጋንንት በስተቀር በቅርብ ያሉ ሁሉ ይሰሙታል።»

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (93) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ በእኒያ በከፈሩት በሙሰይሊመቱል ከዛብና በአብደላሕ ኢብኑ አቢ ሰርህ በተባሉት ሰዎች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (94) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ነድር ኢብኑ ሀሪስ «ላት» እና «ኡዛ» የተባሉ ጣኦቶች ሊሸመግሉኝና ሊጠቅሙኝ ይችላል» በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ሱዩጢ)

۞إِنَّ ٱللَّهَ فَالِقُ ٱلۡحَبِّ وَٱلنَّوَىٰۖ يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ ٱلۡمَيِّتِ وَمُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتِ مِنَ ٱلۡحَيِّۚ ذَٰلِكُمُ
ٱللَّهُۖ فَأَنَّىٰ تُؤۡفَكُونَ ٩٥ فَالِقُ ٱلۡإِصۡبَاحِ وَجَعَلَ ٱلَّيۡلَ سَكَنٗا وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ حُسۡبَانٗاۚ
ذَٰلِكَ تَقۡدِيرُ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡعَلِيمِ ٩٦ وَهُوَ ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلنُّجُومَ لِتَهۡتَدُواْ بِهَا فِي ظُلُمَٰتِ
ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِۗ قَدۡ فَصَّلۡنَا ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٩٧ وَهُوَ ٱلَّذِيٓ أَنشَأَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ
فَمُسۡتَقَرّٞ وَمُسۡتَوۡدَعٞۗ قَدۡ فَصَّلۡنَا ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَفۡقَهُونَ ٩٨ وَهُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ
مَآءٗ فَأَخۡرَجۡنَا بِهِۦ نَبَاتَ كُلِّ شَيۡءٖ فَأَخۡرَجۡنَا مِنۡهُ خَضِرٗا نُّخۡرِجُ مِنۡهُ حَبّٗا مُّتَرَاكِبٗا وَمِنَ
ٱلنَّخۡلِ مِن طَلۡعِهَا قِنۡوَانٞ دَانِيَةٞ وَجَنَّٰتٖ مِّنۡ أَعۡنَابٖ وَٱلزَّيۡتُونَ وَٱلرُّمَّانَ مُشۡتَبِهٗا وَغَيۡرَ
مُتَشَٰبِهٍۗ ٱنظُرُوٓاْ إِلَىٰ ثَمَرِهِۦٓ إِذَآ أَثۡمَرَ وَيَنۡعِهِۦٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكُمۡ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ٩٩

**95-99.** አላህ የቅንጣትንና የፍሬን አጥንት ፈልቃቂ ነው። ከሙት ነገር ሕያውን ያወጣል። ከሕያውም ነገር ሙትን አውጭ ነው። ይህ አላህ ጌታችሁ ነው። ታዲያ እንዴት ከእውነት ትሸሻላችሁ፣ እርሱም ጎሕን ከጽልመት ፈልቃቂ ሌሊቱን ማረፊያ ፀሐይንና ጨረቃን ለጊዜ ስሌት መጠቀሚያ ያደረገ አምላክ። ይህ የዚያ ኃያልና ጥበበኛ የሆነው አምላክ ውሳኔ ነው። እርሱ (አላህ) ያ በየብስና በባህር በጨለማዎች ውስጥ ራሳችሁን መምራት ትችሉ ዘንደ ከዋክብትን የፈጠረላችሁ አምላክ ነው። ለሚያውቁ ሰዎች ሁሉ አንቀፆችን በሚገባ አብራርተናል። (ሰዎች ሆይ)፣ እርሱ (አላህ) ያ ከአንዲት ነፍስ ያስገኛችሁ አምላክ ነው። በማሕፀን ውስጥ ማረፊያንና ምድር ላይም መኖሪያን አመቻቸላችሁ። መገንዘብ ለሚችሉ ሰዎች ሁሉ አንቀፆችን በሚገባ አብራርተናል። (እርሱም) (አላህ) ያ ከሰማይ ውሃን ያወረደ አምላክ ነው። በርሱም የሁሉንም ዓይነት እፅዋት አበቀልን። የተደራረበ ቅንጣት ከእርሱ የምናወጣበትን የሆነ ለምለም አዝመራም ከርሱ አወጣን። ከዘንባባ ከእንቡጥም የተቀራረቡ የሆኑ ዘለላዎችን አወጣን። የወይን አትክልት ቦታዎችን አዘጋጀን። ቅጠሎቻቸው የሚመሳሰሉ ፍሬዎቻቸው ግን የማይመሳሰሉ የሆኑትን የዘይቱንና የሩማን እፅዋትም ከሰማይ ባወረድነው ዝናብ አበቀልን። (የሰው ልጆች ሆይ)፣ ፍሬውን ባፈራና በበሰለ ጊዜ ተመልከቱት እጅግ አስደናቂ ሆኖ ታገኙታላችሁ። በነኝህ ክስተቶች ውስጥ በትክክል በአላህ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ በርካታ ተአምራት አሉ።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (99) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- «እርሱ ያ ከሰማይ ውሃን ያወረደ ነው። በርሱም የነገሩን ሁሉ በቃይ አወጣን፤ የተደራረበንም ቅንጣት ከእርሱ የምናወጣ የሆነ ለምለም አዝመራ ከእርሱ አወጣን ከዘንባባም ከእንቡጧ የተቀራረቡ የሆኑ ዘለላዎች አሉ። ከወይኖች ከወይራ ከሩማንም ቅጠላቸው ተመሳሳይና ፍሬያቸው የማይመሳሰል ሲሆኑ አትክልቶችን አወጣን። ባፈራ ጊዜ ወደ ፍሬውና ወደ መብሰሉ ተመልከቱ በይሃችሁ ለሚያምኑ ህዝቦች ምልክቶች አሉ»

وَجَعَلُواْ لِلَّهِ شُرَكَآءَ ٱلْجِنَّ وَخَلَقَهُمْۖ وَخَرَقُواْ لَهُۥ بَنِينَ وَبَنَٰتِۭ بِغَيْرِ عِلْمٖۚ سُبْحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ
عَمَّا يَصِفُونَ ﴿١٠٠﴾ بَدِيعُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِۖ أَنَّىٰ يَكُونُ لَهُۥ وَلَدٞ وَلَمْ تَكُن لَّهُۥ صَٰحِبَةٞۖ
وَخَلَقَ كُلَّ شَيْءٖۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيْءٍ عَلِيمٞ ﴿١٠١﴾

**100-101.** ሰዎች የፈጠራቸው አላህ ሲሆን አጋንንትን በመታዘዝ ለሱ ተጋሪዎች አደረጉ። ወንዶች ልጆችና ሴቶች ልጆችንም አለው በማለት ያለ ዕውቀት በእርሱ ላይ ቀጠፉ። አላህ ጥራት የተገባውና ከሚሉት ነገር ሁሉ የላቀ ነው። እርሱ ሰማያትንና ምድርን ያለ ብጤ ፈጣሪ ነው። ለእርሱም ሚስት የሌለው ሲሆን እንዴት ለእርሱ ልጅ ይኖረዋል? ሁሉንም ነገር ፈጠረ። እርሱ ሁሉንም ነገር አዋቂ ነውና።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (100) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አላህና ዲያቢሎስ ወንድማማቾች ናቸው። አላህ ሰውንና እንስሳትን ሲፈጥር ዲያቢሎስ ደግሞ እባቦችንና፤ የዱር አውሬዎችንና ጊንጦች ፈጠረ» ይሉ የነበሩ ከሓዲያንን ለማስተባበልና ለማስተማር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)።

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (91-101) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህን በትክክል የሚያውቁ ነብያት ያስተማሩትን ሁሉ ያውቃሉ፤
2. ነብይ ነኝ በማለት በአላህ ላይ ውሸት መዋሸት ከግፍ አይነቶች ሁሉ ከፍተኛው እንደሆነ፤
3. በመሬት ላይ ግፍ የሰሩ ሁሉ ጭንቀቱ በጣረሞት ላይ እያሉም እንደሚያጋጥማቸው፤
4. የቂያማ ዕለት የሰው ልጅ በዱንያ ላይ የሰራው መልካም ካልሆነ ምንም እንደማይጠቅመው፤
5. በአላህ ፍጡሮች እንድንመራመር፤
6. ትክክለኛ እምነት ማለት ተረድተውና ተገንዝበው የያዙት እንጂ ሌላን በመከተል የሚያዝ አለመሆኑ፤
7. ኢስላም አዕምሮን እንደሚያከብርና ለሚያምነውና ለማያምነው ጉዳይ አዕምሮን በአግባቡ መጠቀም እንዳለበት፤
8. አላህ ከአጋር፤ ከልጅ፤ ከሚመስለው የፀዳ መሆኑን እንማራለን።

ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ خَٰلِقُ كُلِّ شَيْءٖ فَٱعْبُدُوهُۚ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٖ وَكِيلٞ ﴿١٠٢﴾
لَّا تُدْرِكُهُ ٱلْأَبْصَٰرُ وَهُوَ يُدْرِكُ ٱلْأَبْصَٰرَۖ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٠٣﴾

**102-103.** ይህ ጌታችሁ አላህ ነው። ከእርሱ በስተቀር አምላክ የለም። ሁሉን ነገር ፈጣሪ ነው። ስለዚህ እርሱን ብቻ ተገዙት። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነውና። አይኖች አያገኙትም (አያዩትም)። እርሱ ግን አይኖችን ያያል። እርሱም ሩህሩህና ውስጠ አዋቂ ነው።

قَدْ جَآءَكُم بَصَآئِرُ مِن رَّبِّكُمْۖ فَمَنْ أَبْصَرَ فَلِنَفْسِهِۦۖ
وَمَنْ عَمِيَ فَعَلَيْهَاۚ وَمَآ أَنَا۠ عَلَيْكُم بِحَفِيظٍ ﴿١٠٤﴾

**104.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታችሁ ዘንድ ብርሃኖች በእርግጥ መጡላችሁ። እውነቱን የተመለከተ ሰው ጥቅሙ ለነፍሱ ብቻ ነው። የታወረም ሰው ጉዳቱ በራሱ ላይ ብቻ ነው። እኔም በእናንተ ላይ ጠባቂ አይደለሁም (በላቸው)።

وَكَذَٰلِكَ نُصَرِّفُ ٱلْأَيَٰتِ وَلِيَقُولُواْ دَرَسْتَ وَلِنُبَيِّنَهُۥ لِقَوْمٍ يَعْلَمُونَ ﴿١٠٥﴾

**105.** ልክ እንደዚሁም እንዲገመግሙና ያለፉትን መጽሐፍ አጥንተሃል እንዲሉ ለሚያውቁ ህዝቦች ቁርአንን እንድናብራራ አንቀፆችን እንገልፃለን።

ٱتَّبِعْ مَآ أُوحِيَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ وَأَعْرِضْ عَنِ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٠٦﴾
وَلَوْ شَآءَ ٱللَّهُ مَآ أَشْرَكُواْۗ وَمَا جَعَلْنَٰكَ عَلَيْهِمْ حَفِيظًاۖ وَمَآ أَنتَ عَلَيْهِم بِوَكِيلٍ ﴿١٠٧﴾
وَلَا تَسُبُّواْ ٱلَّذِينَ يَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ فَيَسُبُّواْ ٱللَّهَ عَدْوًۢا بِغَيْرِ عِلْمٍۗ كَذَٰلِكَ زَيَّنَّا
لِكُلِّ أُمَّةٍ عَمَلَهُمْ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّهِم مَّرْجِعُهُمْ فَيُنَبِّئُهُم بِمَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿١٠٨﴾

**106-108.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን ብቻ ተከተል። ከእርሱ በስተቀር ትክክለኛ ማንም አምላክ የለም። አጋሪዎችንም ተዋቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በፈለገ ኖሮ እነርሱ ጣኦትን ባላጋሩ ነበር። በእነርሱም ላይ ጠባቂ አላደረግንህም። አንተም በእነርሱ ላይ ኃላፊ አይደለህም። (ሙስሊሞች ሆይ!) እነዚያን ከአላህ ሌላ የሚገዟቸውን ጣዖታትን አትስደቡ። እነርሱም ድንበርን በማለፍ ያለ እውቀት አላህን ይሰድባሉና። ልክ እንደዚሁ ለህዝቦች ሁሉ ስራቸውን ደግ አስመሰልንላቸው። ከዚያ መመለሻቸው ወደ ጌታቸው ነው። ይሰሩት የነበሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (108) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት ተብሎ ከተወሩት መካከል፡- የበነብዩ (ﷺ) አጎት አቡጧሊብ ለመሞት በማጣጣር ላይ እያሉ ቁረይሾች ነብዩን በተመለከተ አንድ አስቸኳይ ስብሰባ አደረጉ። የስብሰባውም ውጤት «አቡጧሊብ ከመሞቱ በፊት እንግባና የወንድምህ ልጅ ከልክልልን እንበለው። ምክንያቱም ከሞተ በኋላ የገደልነው እንደሆነ አረቦች «አቡጧሊብ በነበረበት ጊዜ አክብረውት ኖረው ሲሞት ገደሉት በማለት ያወሩብናል» የሚል ነበር። ወደ አቡጧሊብ በመሄድም «ታላቃችንና አለቃችን ነህ። ሙሐመድ ደግሞ እኛንም ሆነ አማልዕክቶቻችንን አሰቃየን። ስለዚህ አንተ ሳለህ ጠርተኸው የእኛን አማልዕክቶች እንዳይነካኢብኑ እኛም የእሱን ጣዖት እንዳንነካበት ብታደርግ ምን ይመስልሀል?» አሏቸው። አቡጧሊብም ሙሐመድን (ﷺ) በማስጠራት «ሙሐመድ ሆይ! እነዚህ ዘመዶችህና አጎቶችህ ናቸው አሉ።» ነብዩም (ﷺ) «ምን ይፈልጋሉ?» ሲሏቸው እኛና አማልዕክቶቻችንን እንድትተወን። እኛም አንተንና አምላክህን ልንተው ነው።» አሏቸው። በዚህ ጊዜ አቡጧሊብ ጣልቃ በመግባት «ሙሐመድ ሆይ! ዘመዶችህ አሳማኝ ነጥብ ነው ያመጡት ብትቀበላቸውስ» ሲሏቸው ነብዩ (ﷺ) «ይህን ባደርግላችሁ አንዲት ቃል ትገቡልኛላችሁ። በእሷም ከተናገራችሁ አረኢብኑ ትገዛላችሁ። ከአረብ ውጪ ያለውም በስራችሁ ይሆናል አሏቸው። አቡጀህል እረ አስርም እንጨምርልሀለን ግን ምንድናት እሷ አለ» ነብዩ (ﷺ) «ላኢላሀ ኢለላህ በሉ» አሏቸው። ፊታቸው ተጨማደደ እምቢም አሉ። በዚህ ጊዜ አቡጧሊብ «የወንድሜ ልጅ እስኪ ሌላ ጠይቃቸው ይህችንማ ፈሯት እኮ» ሲሏቸው ነብዩ (ﷺ) መለስ አድርገው «አይ አጎቴ ፀሐይን አምጥተው በእጇ ቢያስጨብጡኝ ከእሷ ሌላ ምንም አልናገርም» ሲሉ መኮች «አምላኮቻችንን ከመስደብ ካልታቀብክ አንተንም የሚያዝህንም እንሰድባችኋለን» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ኢብኑ ከሲር እና ዋሒዲ)

وَأَقْسَمُوا۟ بِٱللَّهِ جَهْدَ أَيْمَـٰنِهِمْ لَئِن جَآءَتْهُمْ ءَايَةٌ لَّيُؤْمِنُنَّ بِهَا ۚ قُلْ إِنَّمَا ٱلْـَٔايَـٰتُ عِندَ ٱللَّهِ ۖ
وَمَا يُشْعِرُكُمْ أَنَّهَآ إِذَا جَآءَتْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٠٩﴾

**109.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተዐምር ብትመጣላቸው በእርሷ በቁርጥ እንደሚያምኑ ጥብቅ መሀላዎቻቸውን በአላህ ማሉ። ታዐምራት ሁሉ የሚከሰቱት በአላህ ፈቃድ ብቻ ነው በላቸው። እርሷ በመጣች ጊዜም አለማመናቸውን ወይም ማመናቸውን ምን አሳወቃችሁ? በላቸው።

وَنُقَلِّبُ أَفْـِٔدَتَهُمْ وَأَبْصَـٰرَهُمْ كَمَا لَمْ يُؤْمِنُوا۟ بِهِۦٓ أَوَّلَ مَرَّةٍ
وَنَذَرُهُمْ فِى طُغْيَـٰنِهِمْ يَعْمَهُونَ ﴿١١٠﴾

**110.** በመጀመሪያ ጊዜ በእርሱ እንዳላመኑ ሁሉ ልቦቻቸውንና አይኖቻቸውን እናገላብጣለን። በጥመታቸውም ውስጥ የሚዋልሉ ሲሆኑ እንተዋቸዋለን።

۞ وَلَوْ أَنَّنَا نَزَّلْنَآ إِلَيْهِمُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةَ وَكَلَّمَهُمُ ٱلْمَوْتَىٰ وَحَشَرْنَا عَلَيْهِمْ كُلَّ شَىْءٍ قُبُلًا مَّا كَانُوا۟
لِيُؤْمِنُوٓا۟ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ يَجْهَلُونَ ﴿١١١﴾ وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَا لِكُلِّ نَبِىٍّ عَدُوًّا
شَيَٰطِينَ ٱلْإِنسِ وَٱلْجِنِّ يُوحِى بَعْضُهُمْ إِلَىٰ بَعْضٍ زُخْرُفَ ٱلْقَوْلِ غُرُورًا ۚ وَلَوْ شَآءَ رَبُّكَ مَا
فَعَلُوهُ ۖ فَذَرْهُمْ وَمَا يَفْتَرُونَ ﴿١١٢﴾ وَلِتَصْغَىٰٓ إِلَيْهِ أَفْـِٔدَةُ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْءَاخِرَةِ وَلِيَرْضَوْهُ
وَلِيَقْتَرِفُوا۟ مَا هُم مُّقْتَرِفُونَ ﴿١١٣﴾

**111-113.** *እኛም ወደ እነርሱ መላዕክትን ባወረድን ኖሮ ሙታንን ባነጋገሩዋቸውና ነገሩን ሁሉ በቡድን በቡድን አድርገን በነሱ ላይ በሰበሰብንም ኖሮ አላህ ካልሻ በስተቀር የሚያምኑ ባልሆኑ ነበር። ግን አብዛኞቻቸው ይህንን እውነታ ይስታሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እንደዚሁም ለነብዮች ሁሉ ከሰውና ከጋኔን የሆኑን ሰይጣናት ጠላት አደረግን። ከፊላቸው ወደ ከፊሉ ለማታለል የተዋበን ንግግር ይጥላሉ። ጌታህ በፈለገ ኖሮ ይህን ፀያፍ ተግባር ባልሰሩት ነበር። ከቅጥፈታቸውም ጋር ተዋቸው። (የሚጥሉም ሊያታልሉ) የነዚያም በመጨረሻይቱ ህይወት የማያምኑት ሰዎች ልቦች ወደ እርሱ እንዲያዘነብሉ እነርሱ ይቀጥፉ የነበሩትንም እንዲቀጥፉ ነው።

✷ ክፍል ስምንት

ከቤት እንስሳዎች ምዕራፍ ከ (109-111) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የመካ መሪዎች «ነብዩ (ﷺ) ነብዩ ሙሳ ተዓምራቸው ዘንግ እንደነበረች። በእርሷ ድንጋይ ሲመቱባት ተሰንጥቆ ምንጭ ሆነ። ነብዩ ዒሳም የሞተን የማዳን ተአምር ተሰጥተው ነበር። ለሰሙዶች ተአምረኛ ግመል ተሰጥታቸው ነበር። ትላለህ እስቲ ለአንተ ነብይነት ማስረጃ የሚሆን ነገር አምጣልን» አሏቸው ነብዩ (ﷺ) «ምን እንዳመጣላችሁ ትፈልጋላችሁ» ሲሉ ጠየቋቸው «የሶፋን ጋራ ወርቅ እንድታደርጉልን ነዋ» አሏቸው ነብዩ «ካደረኩኝ ታምኑልኛላችሁ» በማለት መልሰው ጠየቋቸው። እነሱም ወላሂ ሁላችንም አንድ ሳይቀር እንከተልሃለን አሉ። በዚህ ጊዜ ነብዩ (ﷺ) ጌታቸውን መለመን ጀመሩ። ጅብሪል መጣና «ሙሐመድ ሆይ! ከፈለክ የሶፋ ጋራ ወርቅ ይሆናል» ነገር ግን ያላመኑ እንደሆነ አይቀጡ ቅጣት ነው የምንቀጣቸው። ከፈለክ ደግሞ ከመሃላቸው አላህ የሻለት እስከሚመለስ ድረስ» በማለት ሲያማርጣቸው ነብዩ (ﷺ) ሁለተኛውን ምርጫ በመምረጥ ላይ ሳሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፣ ኢብኑ ከሲር፣ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَفَغَيْرَ ٱللَّهِ أَبْتَغِى حَكَمًا وَهُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ إِلَيْكُمُ ٱلْكِتَٰبَ مُفَصَّلًا ۚ وَٱلَّذِينَ ءَاتَيْنَٰهُمُ
ٱلْكِتَٰبَ يَعْلَمُونَ أَنَّهُۥ مُنَزَّلٌ مِّن رَّبِّكَ بِٱلْحَقِّ ۖ فَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُمْتَرِينَ ﴿١١٤﴾ وَتَمَّتْ
كَلِمَتُ رَبِّكَ صِدْقًا وَعَدْلًا ۚ لَّا مُبَدِّلَ لِكَلِمَٰتِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ﴿١١٥﴾

**114-115.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱ ያ መጽሐፉን የተብራራ ሆኖ ወደእናንተ ያወረደ ሲሆን ከአላህ ሌላ ዳኛን እፈልጋለሁን? በላቸው። እነዚያንም መጽሐፉን የሰጠናቸው ሰዎች ሁሉ ቁርኣን ከጌታህ ዘንድ በእውነት የተወረደ መሆኑን በትክክል ያውቃሉ። እናም ከተጠራጣሪዎቹ አትሁን። ((መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)) የጌታህ ቃላት እውነተኛና ትክክለኛ ስትሆን ተፈፀመች። ለቃላቱ ምንጊዜም ለዋጭ የለም። እርሱ ሁሉን ሰሚና ሁሉን አዋቂ ነውና።

وَإِن تُطِعۡ أَكۡثَرَ مَن فِي ٱلۡأَرۡضِ يُضِلُّوكَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِۚ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَإِنۡ هُمۡ إِلَّا يَخۡرُصُونَ ﴿١١٦﴾ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعۡلَمُ مَن يَضِلُّ عَن سَبِيلِهِۦۖ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُهۡتَدِينَ ﴿١١٧﴾

**116-117.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ካሉት ሰዎች መካከል አብዛኞቹን ብትከተል የአላህን መንገድ ያሳስቱሀል። ጥርጣሬን እንጂ ሌላን አይከተሉምና። እነርሱም የሚዋሹ እንጂ ሌላ አይደሉም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ከመንገዱ የሚሳሳቱትን አዋቂ ነው። እርሱም ተመሪዎቹን እንዲሁ አዋቂ ነው።

فَكُلُواْ مِمَّا ذُكِرَ ٱسۡمُ ٱللَّهِ عَلَيۡهِ إِن كُنتُم بِـَٔايَٰتِهِۦ مُؤۡمِنِينَ ﴿١١٨﴾ وَمَا لَكُمۡ أَلَّا تَأۡكُلُواْ مِمَّا ذُكِرَ ٱسۡمُ ٱللَّهِ عَلَيۡهِ وَقَدۡ فَصَّلَ لَكُم مَّا حَرَّمَ عَلَيۡكُمۡ إِلَّا مَا ٱضۡطُرِرۡتُمۡ إِلَيۡهِۗ وَإِنَّ كَثِيرٗا لَّيُضِلُّونَ بِأَهۡوَآئِهِم بِغَيۡرِ عِلۡمٍۚ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُعۡتَدِينَ ﴿١١٩﴾ وَذَرُواْ ظَٰهِرَ ٱلۡإِثۡمِ وَبَاطِنَهُۥٓۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَكۡسِبُونَ ٱلۡإِثۡمَ سَيُجۡزَوۡنَ بِمَا كَانُواْ يَقۡتَرِفُونَ ﴿١٢٠﴾ وَلَا تَأۡكُلُواْ مِمَّا لَمۡ يُذۡكَرِ ٱسۡمُ ٱللَّهِ عَلَيۡهِ وَإِنَّهُۥ لَفِسۡقٞۗ وَإِنَّ ٱلشَّيَٰطِينَ لَيُوحُونَ إِلَىٰٓ أَوۡلِيَآئِهِمۡ لِيُجَٰدِلُوكُمۡۖ وَإِنۡ أَطَعۡتُمُوهُمۡ إِنَّكُمۡ لَمُشۡرِكُونَ ﴿١٢١﴾

**118-121.** በአናቅፅም ትክክለኛ አማኞች እንደሆናችሁ ሲታረድ የአላህ ስም በእርሱ ላይ ከተወሳበት እንስሳ ብሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱን መብላት ካልተገደዳችሁበት በስተቀር በእናንተ እርም የተደረገውን ለእናንተ አላህ በእርግጥ የዘረዘረ ሲሆን ከዚያ በእርሱ ላይ የአላህ ስም ከተጠራበት የማትበሉት ለናንተ ምን ምክንያት አላችሁ? ብዙዎቹ ያለ እውቀት በዝንባሌዎቻቸው ብቻ ያሳስታሉ። ጌታህ ወሰን አላፊዎቹን አዋቂ ነውና። የኃጢአትን ግልፁንም ድብቁንም ተው። እነዚያ ኃጢአትን የሚሰሩ ሰዎች

ሁሉ ይሰሩት በነበሩበት ነገር በእያንዳንዱ በእርግጥ ይቀጣሉ። (ሙስሊሞች ሆይ!) በእርሱ ላይ የአላህ ስም ካልተጠራበት ነገር አትብሉ። እርሱም በእርግጥ የአመፅ ነው። ሰይጣናትም ወደ ወዳጆቻቸው በክትን በመብላት ይከራከሯችሁ ዘንድ ያሾከሹካሉ። ታዲያ ብትታዘዟቸው✳ በእርግጥ አጋሪዎች ናችሁ።

✳ ኢማም አህመድ፤ አት- ቲርሚዚይና ኢብኑ ጀሪር እንደዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ)፡- «ከርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንዱን አምላክ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆን ሊቃውንቶቻቸውንና መነኮሳታቸውን የመርየም ልጅ አል. መሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከሚያጋሩትም ሁሉ የጠራ ነው።» (አትተውባህ፡ 31) የሚለውን የቁርኣን አንቀፅ እያነበቡ ሳለ ዐድይ ኢብኑ ሓቲም እንዲህ አሏቸው። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነሱ ግን እነርሱን አያመልኳቸውም።» ነብዩም «በትክክል ያመልኳቸዋል። ምክንያቱም ራቢዎችና ቀሳውስቶች ፊፅሞ ክልክል የሆኑትን ተግባራት የተፈቀዱ ያደርጋሉ። የተፈቀዱትን ተግባራት ደግሞ እንዳልተፈቀዱ (ፊፅሞ ክልክል) እንደሆኑ ያደርጋሉ። እነርሱም ና ክርስቲያኖችም የእነርሱን ቃል ይከተላሉ። ይህንን በማድረጋቸውም በእርግጥ ያመልኳቸዋል።» (በተፍሲር አጥጦበሪይ እንደሰፈረው)

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (118) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ ሰዎች ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት እኛ የምንገድለውን እየበላን ፈጣሪ የገደለውን ግን አንበላምን?» በማለት ሲጠይቋቸው የወረዱ አናቅፅ ናቸው። (አቡዳውድ፤ ቲርሚዚ፤ ሃኪም እና ሱዩጢ)

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (121) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ መሪዎች ነብዩን (ﷺ) «የሞተችን ፍየል ማነው የገደላት» በማለት ጠይቀው «አላህ ነዋ» ሲሏቸው «አንተና ባልደረቦችህ የገደላችሁትን መመገብ ይፈቀዳል እያልክ አላህ የገደለውን ግን አይፈቀድም ትላለህ» በማለት ሲያንጓጥጧቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ፤ ኢብኑልጀውዚ እና ዋሒዲ)

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (102-118) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ብቸኛ አምላክ መሆኑን፤
2. አላህ ሁሉን የሚያውቅ መሆኑን፤
3. ቀናውን መንገድ የመከተሉ ጥቅም ለባለቤቱ እንደሆነ ሁሉ መጥፎን መንገድ መከተልም ጉዳቱ ለራሱ ለባለቤቱ እንደሆነ፤
4. የሌሎችን አማልዕክት መስደብ አግባብ እንዳልሆነ፤
5. ቀናውን መንገድም ሆነ የተሳሳተውን መንገድ የፈጠረው አላህ ብቻ መሆኑን፤
6. የሰው ሰይጣናት ከጋኔን ሰይጣናት እንደሚከፉ፤
7. አላህ ሰዎችን ከቀናው መንገድ የሚያጠሙትን ሰዎች እንደሚያውቅ፤
8. አምልኮት ለወንጀል የሚያበቃ የሚያደርስ ከሆነ መተው ግዴታ እንደሆነ፤
9. ለመጥፎ ዉጤት የሚያደረስ ነገር ሁሉ መጥፎ መሆኑን፤
10. የሸር በሮችን መዝጋት ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

أَوَمَن كَانَ مَيْتًا فَأَحْيَيْنَٰهُ وَجَعَلْنَا لَهُۥ نُورًا يَمْشِى بِهِۦ فِى ٱلنَّاسِ كَمَن مَّثَلُهُۥ فِى ٱلظُّلُمَٰتِ
لَيْسَ بِخَارِجٍ مِّنْهَا ۚ كَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِلْكَٰفِرِينَ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿١٢٢﴾ وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَا فِى كُلِّ
قَرْيَةٍ أَكَٰبِرَ مُجْرِمِيهَا لِيَمْكُرُوا۟ فِيهَا ۖ وَمَا يَمْكُرُونَ إِلَّا بِأَنفُسِهِمْ وَمَا يَشْعُرُونَ ﴿١٢٣﴾ وَإِذَا
جَآءَتْهُمْ ءَايَةٌ قَالُوا۟ لَن نُّؤْمِنَ حَتَّىٰ نُؤْتَىٰ مِثْلَ مَآ أُوتِىَ رُسُلُ ٱللَّهِ ۘ ٱللَّهُ أَعْلَمُ حَيْثُ يَجْعَلُ
رِسَالَتَهُۥ ۗ سَيُصِيبُ ٱلَّذِينَ أَجْرَمُوا۟ صَغَارٌ عِندَ ٱللَّهِ وَعَذَابٌ شَدِيدٌۢ بِمَا كَانُوا۟ يَمْكُرُونَ ﴿١٢٤﴾

**122-124.** ሙት የነበረና ከዚያ ህያው ያደረግነው ለርሱም በሰዎች መካከል በእርሱ የሚሄድበትን ብርሃን ያደረግንለት ሰው በጨለማዎች ውስጥ ምንጊዜም የማይወጣ ሆኖ እንዳለ ሰው ብጤ ነውን? ልክ እንደዚሁ ለከሓዲያን ሁሉ ይሰሩት የነበሩት ነገር ተዋበላቸው፡፡ ልክ እንደዚሁ በየከተማይቱ በውስጧ ያሴሩ ዘንድ ታላላቅ ተንኮለኞችን ፈጠርን (አደረግን)፡፡ በነፍሶቻቸው ላይ እንጂ በሌላ ላይ አያሴሩም፡፡ ግን ይህን እውነታ አያውቁም፡፡ ተዐምርም በመጣላቸው ጊዜ የአላህ መልዕክተኞች የተሰጡትን ብጤ እስክንሰጥ ድረስ በፍፁም አናምንም አሉ፡፡ አላህ መልዕክቱን የሚያደርግበትን ስፍራ አዋቂ ነው፡፡ እነዚያን በአላህ ያመፁ ሰዎች ይዶልቱት በነበሩት ነገር አላህ ዘንድ ውርደትና ብርቱ ቅጣት ያገኛቸዋል፡፡

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (122) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሀምዛ ከመስለማቸው በፊት አንድ ቀን ከአውሬ አደን ሲመለሱ የወንድማቸው ልጅ የሆኑት ነብዩ (ﷺ) ላይ አቡጀህል ያደረሰው ጥቃት ሰምተው በጣም ተቆጡ፡፡ ወደ አቡጀህል በመሄድ አቡጀህልን በሰይፋቸው ደንደስ ወቀሩት፡፡ እርሱም «ሀምዛ ሆይ! አይታይህም እንዴ ሙሐመድ እኮ አዋቂዎቻችንን ሞኝ አድርጎ፤ አምላኮቻችንንም ሰድቦ፤ አባቶቻችንንም ተቃርኖ በጠላትነት ተሰልፏል» ሲል የነብዩን (ﷺ) ጥፋቶች ዘረዘረ፡፡ ሀምዛ ግን የእርሱ አቤቱታና «ወቀሳ ከግምት ውስጥ የማይገባና የነብዩ (ﷺ) ጥሪና አቋም ትክክል መሆኑን ገለፁለትና ከእናንተ የበለጠ ሞኝ የለም፡፡ ከአላህ ሌላ አማልዕክትን የተገዛችሁ ትጃጃላላችሁ፡፡ እኔ ከዛሬ ጀምሮ ከአንድ አምላክ በስተቀር ሌላ አምላክ እንደሌለ ሙሐመድም የእርሱ መልዕክተኛ እና አገልጋይ መሆኑን እመሰክራለሁ፡፡ በማለት ኢስላምን መቀበላቸውን ይፋ ሲያደርጉ ይህ አንቀፅ ወረደ፡፡ (ሱዩጢ፤ ኢብኑ ከሲርና ኢብኑ-ልጀውዚ)

فَمَن يُرِدِ ٱللَّهُ أَن يَهْدِيَهُۥ يَشْرَحْ صَدْرَهُۥ لِلْإِسْلَٰمِ ۖ وَمَن يُرِدْ أَن يُضِلَّهُۥ يَجْعَلْ صَدْرَهُۥ ضَيِّقًا
حَرَجًا كَأَنَّمَا يَصَّعَّدُ فِى ٱلسَّمَآءِ ۚ كَذَٰلِكَ يَجْعَلُ ٱللَّهُ ٱلرِّجْسَ عَلَى ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٢٥﴾

**125.** አላህም ሊመራው የሚሻውን ሰው ሁሉ ልቡን ለኢስላም ይከፍትለታል፡፡ ሊያጠመውም የሚሻውን ሰው ደግሞ ልቡን ጠባብና ተቸጋሪ ወደ ሰማይ ለመውጣት እንደሚታገል ያደርገዋል፡፡ ልክ እንደዚሁ አላህ በእነዚያ በትክክል በማያምኑት* ሰዎች ላይ ርክሰትን ያደርጋል፡፡

✴ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሙዓዊያህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ሚንበር ላይ ሆነው እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ «አላህ ለአንድ ሰው መልካም ሊውልለት ከፈለገ በሃይማኖቱ ጥልቅ አዋቂ ያደርገዋል። እኔ በእርግጥ አስተላላፊ ነኝ። ነገር ግን ሰጪ አላህ ነው። አስተውል! እነዚህ ሕዝቦች እውነተኛ ሙስሊሞች ሆነው አላህን ብቻ የሚያመልኩ ሰዎች ለአላህ ትዕዛዛት ቅን ሆነው ይቆያሉ። የፍርዱ ቀን እስኪመጣ ድረስ እነሱንም በሚቀናቀናቸው ወገን በኩል ምንም ጉዳት አይደርስባቸውም»

وَهَٰذَا صِرَٰطُ رَبِّكَ مُسْتَقِيمًاۗ قَدْ فَصَّلْنَا ٱلْءَايَٰتِ لِقَوْمٍ يَذَّكَّرُونَ ﴿١٢٦﴾
۞ لَهُمْ دَارُ ٱلسَّلَٰمِ عِندَ رَبِّهِمْۖ وَهُوَ وَلِيُّهُم بِمَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿١٢٧﴾

**126-127.** ይህ ያለህበት መንገድ ቀጥተኛ ሲሆን የጌታህ መንገድ ነው። ለሚያስታውሱ ህዝቦች ሁሉ አንቀፆችን እርግጥ ዘርዝረናል። ለእነርሱም በጌታቸው ዘንድ የሰላም ሀገር አለላቸው። እርሱም (ጌታህ) ይሰሩት በነበሩት ምክንያት ረዳታቸው ነው።

وَيَوْمَ يَحْشُرُهُمْ جَمِيعًا يَٰمَعْشَرَ ٱلْجِنِّ قَدِ ٱسْتَكْثَرْتُم مِّنَ ٱلْإِنسِۖ وَقَالَ أَوْلِيَآؤُهُم مِّنَ ٱلْإِنسِ رَبَّنَا ٱسْتَمْتَعَ بَعْضُنَا بِبَعْضٍ وَبَلَغْنَآ أَجَلَنَا ٱلَّذِىٓ أَجَّلْتَ لَنَاۚ قَالَ ٱلنَّارُ مَثْوَىٰكُمْ خَٰلِدِينَ فِيهَآ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۗ إِنَّ رَبَّكَ حَكِيمٌ عَلِيمٌ ﴿١٢٨﴾

**128.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁሉንም በአንድ ቦታ ላይ በሚሰበስባቸው ቀን (የሚሆነውን አስታውስ)። የአጋንንት ጭፍሮች ሆይ፣ ከሰዎች ጭፍራን በማጥመም በእርግጥ አበዛችሁ ይባላሉ። ከሰዎችም መካከል የሆኑት ወዳጆቻቸው ጌታችን ሆይ! ከፊላችን በከፊሉ ተጠቀመ። ያንን ለእኛ የወሰንክልንን ጊዜያችንን ደረስን ይላሉ። እሳት አላህ የሻው ጊዜ ሲቀር በውስጧ ዘወታሪዎች ስትሆኑ መኖሪያችሁ ናት ይላቸዋል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ጥበበኛና አዋቂ ነው።

وَكَذَٰلِكَ نُوَلِّى بَعْضَ ٱلظَّٰلِمِينَ بَعْضًۢا بِمَا كَانُوا۟ يَكْسِبُونَ ﴿١٢٩﴾

**129.** ልክ እንደዚሁ አንዳንድ በደለኞችን ይሰሩት በነበሩት ጥፋት ምክንያት ከፊሉን በከፊሉ ላይ እንሾማለን።

يَٰمَعْشَرَ ٱلْجِنِّ وَٱلْإِنسِ أَلَمْ يَأْتِكُمْ رُسُلٌ مِّنكُمْ يَقُصُّونَ عَلَيْكُمْ ءَايَٰتِى وَيُنذِرُونَكُمْ لِقَآءَ يَوْمِكُمْ هَٰذَاۚ قَالُوا۟ شَهِدْنَا عَلَىٰٓ أَنفُسِنَاۖ وَغَرَّتْهُمُ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا وَشَهِدُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ أَنَّهُمْ كَانُوا۟

كَٰفِرِينَ ﴿١٣٠﴾ ذَٰلِكَ أَن لَّمْ يَكُن رَّبُّكَ مُهْلِكَ ٱلْقُرَىٰ بِظُلْمٍ وَأَهْلُهَا غَٰفِلُونَ ﴿١٣١﴾
وَلِكُلٍّ دَرَجَٰتٌ مِّمَّا عَمِلُوا۟ وَمَا رَبُّكَ بِغَٰفِلٍ عَمَّا يَعْمَلُونَ ﴿١٣٢﴾ وَرَبُّكَ ٱلْغَنِىُّ ذُو ٱلرَّحْمَةِ
إِن يَشَأْ يُذْهِبْكُمْ وَيَسْتَخْلِفْ مِنۢ بَعْدِكُم مَّا يَشَآءُ كَمَآ أَنشَأَكُم مِّن ذُرِّيَّةِ قَوْمٍ
ءَاخَرِينَ ﴿١٣٣﴾ إِنَّ مَا تُوعَدُونَ لَءَاتٍ وَمَآ أَنتُم بِمُعْجِزِينَ ﴿١٣٤﴾

**130-134.** የአጋንትና የሰዎች ቡድኖች ሆይ! አንቀጾቼን በእናንተ ላይ የሚተርኩ የዚህንም ቀናችሁን ቅጣት ማግኘትን የሚያስፈራሯችሁ ከናንተው የሆኑ መልዕክተኞች አልመጡላችሁም ነበርን? (ይባላሉ)። በነፍሶቻችን ላይ መሰከርን (መጥተውልናል ይላሉ) የቅርቢቱም ሕይወት አታለለቻቸው። በነፍሶቻቸውም ላይ እነርሱ ከሓዲያን የነበሩ መሆናቸውን በራሳቸው መሰከሩ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ የሆነው ጌታህ ከተሞችን ባለቤቶችዋ ዘንጊዎች ሆነው ሳሉ በበደል ምክንያት አጥፊ ባለመሆኑ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለሁሉም በሰሩት ስራ ምክንያት የተበላለጡ ደረጃዎች አሏቸው። ጌታህም ከሚሰሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ በራሱ ተብቃቂ የእዝነት ባለቤት ነው። ቢሻ ከምድረ ገፅ ያጠፋችኋል። ከሌሎች ህዝቦችም ዘሮች እንዳስገኛችሁ ሁሉ ከበኋላችሁ የሚሻውን ሰው ይተካል። (ሰዎች ሆይ!) የምትቀጠሩት ሁሉ በእርግጥ መጪ ነው። እናንተም አምላጮች አይደላችሁም።

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (119-131) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *ሀላልና ሀራምን አላህ በግልፅ እንዳስቀመጠ፤*
2. *ኢስላም የሰው ልጆችን ችግር በትክክል የሚረዳና የሚያገናዝብ ገር ሃይማኖት መሆኑን፤*
3. *ጣኦት አምላኪዎች አማኞችን ሁልጊዜም እንደሚጨቃጨቋቸው፤*
4. *በቁርኣን የሚመራ አማኝ ልቡ ህያው በመሆኑ እውነትና ውሸትን በትክክል እንደሚለይ፤ ከሃዲ ደግሞ ልበ ሙት በመሆኑ እንደማይለይ፤*
5. *ሁሉ ነገር የሚሆነው በአላህ ፈቃድ ብቻ መሆኑን፤*
6. *ሰይጣን መጉዳት የሚችለው ትክክለኛ አማኝ ያልሆኑትን ብቻ መሆኑን፤*
7. *የትንሳኤ ዕለት ጅኖች ከተከተሏቸው ሰዎች ራሳቸውን ነፃ እንደሚያደርጉና ሰዎችም ከተከተሏቸው ጋኔን ራሳቸውን ነፃ እንደሚያደርጉ፤*
8. *ማንም ሰው አላህ በፈጠረው ፍጡር ላይ አንተ የእሳት ነህ አንተ የጀነት ነህ ማለት እንደማይችል፤*
9. *አላህ የሰው ልጆችን እንደስራቸው እንደሚመድባቸው፤*
10. *ግፈኛን የሚደግፍ ሰው ቀድሞ የሚጎዳው ራሱ እንደሆነ እንማራለን።*

قُلْ يَٰقَوْمِ ٱعْمَلُوا۟ عَلَىٰ مَكَانَتِكُمْ إِنِّى عَامِلٌ ۖ فَسَوْفَ تَعْلَمُونَ مَن تَكُونُ لَهُۥ
عَٰقِبَةُ ٱلدَّارِ ۗ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿١٣٥﴾

**135.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ህዝቦቼ ሆይ፣ በችሎታችሁ ላይ ስሩ እኔ በችሎታዬ ላይ ሰሪ ነኝና። ምስጉኒቱ ሀገር ገነት ለእርሱ የምትሆንለት ሰው ማን እንደሆነ ወደፊት ታውቃላችሁ። እነሆ በደለኞች ሁሉ ምንጊዜም አይድኑም በላቸው።

وَجَعَلُوا۟ لِلَّهِ مِمَّا ذَرَأَ مِنَ ٱلْحَرْثِ وَٱلْأَنْعَٰمِ نَصِيبًا فَقَالُوا۟ هَٰذَا لِلَّهِ بِزَعْمِهِمْ وَهَٰذَا لِشُرَكَآئِنَا ۖ فَمَا
كَانَ لِشُرَكَآئِهِمْ فَلَا يَصِلُ إِلَى ٱللَّهِ ۖ وَمَا كَانَ لِلَّهِ فَهُوَ يَصِلُ إِلَىٰ شُرَكَآئِهِمْ ۗ سَآءَ مَا يَحْكُمُونَ ﴿١٣٦﴾

**136.** (አጋሪዎች) ለአላህ ከፈጠረው ከአዝመራውና ከግመል ከከብትና ከፍየል፤ ከበግ ድርሻን ቆንጥረው አደረጉለት። በሀሳባቸውም ይህ የአላህ ነው ይህ ደግሞ ለተጋሪዎቻችን ነው አሉ። ለጣኦት የሆነው ነገር ወደ አላህ ምንጊዜም አይደርስም። ለአላህ የሆነ ነገር ግን ወደ ተጋሪዎቻቸው ይደርሳል አሉ። የሚፈርዱት ፍርድ ከፋ፣

وَكَذَٰلِكَ زَيَّنَ لِكَثِيرٍ مِّنَ ٱلْمُشْرِكِينَ قَتْلَ أَوْلَٰدِهِمْ شُرَكَآؤُهُمْ لِيُرْدُوهُمْ وَلِيَلْبِسُوا۟ عَلَيْهِمْ
دِينَهُمْ ۖ وَلَوْ شَآءَ ٱللَّهُ مَا فَعَلُوهُ ۖ فَذَرْهُمْ وَمَا يَفْتَرُونَ ﴿١٣٧﴾

**137.** ልክ እንደዚሁ ከአጋሪዎቹ ለብዙዎቹ ተጋሪዎቻቸው ጣኦታት ሊያጠፏቸውና ሀይማኖታቸውንም በነሱ ላይ ሊያቀላቅሉባቸው ልጆቻቸውን መግደልን አሳመሩላቸው። አላህ በሻ ኖሮ ይህን (ፀያፍ ተግባር) ባልሰሩት ነበር። እናም ከቅጥፈታቸው ጋር ተዋቸው።

وَقَالُوا۟ هَٰذِهِۦٓ أَنْعَٰمٌ وَحَرْثٌ حِجْرٌ لَّا يَطْعَمُهَآ إِلَّا مَن نَّشَآءُ بِزَعْمِهِمْ وَأَنْعَٰمٌ حُرِّمَتْ ظُهُورُهَا
وَأَنْعَٰمٌ لَّا يَذْكُرُونَ ٱسْمَ ٱللَّهِ عَلَيْهَا ٱفْتِرَآءً عَلَيْهِ ۚ سَيَجْزِيهِم بِمَا كَانُوا۟ يَفْتَرُونَ ﴿١٣٨﴾ وَقَالُوا۟
مَا فِى بُطُونِ هَٰذِهِ ٱلْأَنْعَٰمِ خَالِصَةٌ لِّذُكُورِنَا وَمُحَرَّمٌ عَلَىٰٓ أَزْوَٰجِنَا ۖ وَإِن يَكُن مَّيْتَةً فَهُمْ فِيهِ
شُرَكَآءُ ۚ سَيَجْزِيهِمْ وَصْفَهُمْ ۚ إِنَّهُۥ حَكِيمٌ عَلِيمٌ ﴿١٣٩﴾

**138-139.** በሀሳባቸው እነዚህ እርም የሆኑ ለማዳ እንሰሳና አዝመራ ናቸው። የምንሻለት ሰው እንጂ ሌላ ማንም አይበላቸውም። እነዚህ ደግሞ ጀርባዎቻቸው እርም የተደረገ ለማዳ እንስሳ ናቸው። (አይጫኑም)። እነዚህ (ሲታረዱ) በእነርሱ ላይ የአላህን ስም የማይጠሩባቸውም እንሳሳት ናቸው አሉ። በእርሱ ላይ ለመቅጠፍ ነገሩን ወደ አላህ አስጠጉ። ይቀጥፉት በነበሩት ነገር በእርግጥ ይቀጣቸዋል። በእነዚህ እንስሳት ሆዶች ውስጥ ያለው ፅንሱ ሁሉ ለወንዶቻችን ብቻ በተለይ የተፈቀደ ነው። በሚስቶቻችን ላይ ግን እርም የተደረገ ነው። ሙት ሆኖ ቢወለድ ግን ወንዶቹም ሆነ ሴቶች በእርሱ ላይ ተጋሪዎች ናቸው አሉ። ይህን በመቅጠፋቸው አላህ በእርግጥ ይቀጣቸዋል። እርሱ ጥበበኛና አዋቂ ነውና።

قَدۡ خَسِرَ ٱلَّذِينَ قَتَلُوٓاْ أَوۡلَٰدَهُمۡ سَفَهَۢا بِغَيۡرِ عِلۡمٖ وَحَرَّمُواْ مَا رَزَقَهُمُ ٱللَّهُ ٱفۡتِرَآءً عَلَى ٱللَّهِۚ قَدۡ ضَلُّواْ وَمَا كَانُواْ مُهۡتَدِينَ ١٤٠

**140.** እነዚያ ያለ እውቀት በሞኝነት ልጆቻቸውን የገደሉና አላህም የሰጣቸውን ሲሳይ በአላህ ላይ በመቅጠፍ በራሳቸው ላይ እርም ያደረጉ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ ከሰሩ። በእርግጥ ተሳሳቱም። ወደ ትክክለኛው መንገድም የተመሩ አልነበሩም።

۞وَهُوَ ٱلَّذِيٓ أَنشَأَ جَنَّٰتٖ مَّعۡرُوشَٰتٖ وَغَيۡرَ مَعۡرُوشَٰتٖ وَٱلنَّخۡلَ وَٱلزَّرۡعَ مُخۡتَلِفًا أُكُلُهُۥ وَٱلزَّيۡتُونَ وَٱلرُّمَّانَ مُتَشَٰبِهٗا وَغَيۡرَ مُتَشَٰبِهٖۚ كُلُواْ مِن ثَمَرِهِۦٓ إِذَآ أَثۡمَرَ وَءَاتُواْ حَقَّهُۥ يَوۡمَ حَصَادِهِۦۖ وَلَا تُسۡرِفُوٓاْۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ ٱلۡمُسۡرِفِينَ ١٤١

**141.** እርሱም (አላህ) ያ ዳስ የሚያደርግላቸውንና ዳስ የማያደርግላቸውን አትክልቶች የፈጠረ ነው። ዘንባባንም (የተምርን ዛፍ) አዝመራንም ፍሬዎቹ የተለያዩ ሲሆኑ ወይራንና ሩማንንም ቅጠላቸው ተመሳሳይና ጣዕማቸው የማይመሳሰል ሲሆኑ ፈጠረ። ባፈራ ጊዜ ከፍሬው ብሉ። ባጨዳውም ቀን ተገቢውን ዘካ ለተገቢው ስጡለት። አታባክኑም። አላህ አባካኞችን አይወድምና።

ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ (141) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሳቢት ቢን ቅያስ የተባለ ሰው የአትክልቱን ፍሬ ለቅሞ በአንድ ቀን ጨርሶ ስለዋለ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦባሪ፤ ቁርጡቢ እና ሱዩጢ)

وَمِنَ ٱلۡأَنۡعَٰمِ حَمُولَةٗ وَفَرۡشٗاۚ كُلُواْ مِمَّا رَزَقَكُمُ ٱللَّهُ وَلَا تَتَّبِعُواْ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ إِنَّهُۥ
لَكُمۡ عَدُوّٞ مُّبِينٞ ١٤٢ ثَمَٰنِيَةَ أَزۡوَٰجٖۖ مِّنَ ٱلضَّأۡنِ ٱثۡنَيۡنِ وَمِنَ ٱلۡمَعۡزِ ٱثۡنَيۡنِۗ قُلۡ ءَآلذَّكَرَيۡنِ
حَرَّمَ أَمِ ٱلۡأُنثَيَيۡنِ أَمَّا ٱشۡتَمَلَتۡ عَلَيۡهِ أَرۡحَامُ ٱلۡأُنثَيَيۡنِۖ نَبِّـُٔونِي بِعِلۡمٍ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٤٣
وَمِنَ ٱلۡإِبِلِ ٱثۡنَيۡنِ وَمِنَ ٱلۡبَقَرِ ٱثۡنَيۡنِۗ قُلۡ ءَآلذَّكَرَيۡنِ حَرَّمَ أَمِ ٱلۡأُنثَيَيۡنِ أَمَّا ٱشۡتَمَلَتۡ عَلَيۡهِ
أَرۡحَامُ ٱلۡأُنثَيَيۡنِۖ أَمۡ كُنتُمۡ شُهَدَآءَ إِذۡ وَصَّىٰكُمُ ٱللَّهُ بِهَٰذَاۚ فَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّنِ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ
كَذِبٗا لِّيُضِلَّ ٱلنَّاسَ بِغَيۡرِ عِلۡمٍۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٤٤

**142-144.** (ሰዎች ሆይ)፣ ከለማዳ እንስሳዎችም የሚጫኑትን ፈጠረ። አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይ ብሉ። የሰይጣንንም እርምጃዎች አትከተሉ። እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና። ስምንትን ዓይነቶች፤ ከበግ ሁለትን✶ (ወንድና ሴትን) ከፍየልም ሁለትን ፈጠረ። ከሁለቱም ክፍሎች አላህ ወንዶችን ብቻ እርም አደረገን ወይንስ ሴቶችን ብቻ? ወይስ በእርሱ ላይ የሁለቱ ሴቶች ማህፀኖች ያጠቃለሉትን እርም አደረገ? እውነተኞች እንደሆናችሁ በእውቀት (በአስረጂ) ንገሩኝ በላቸው። ከግመልም ሁለትን፤ ከከብትም ሁለትን ፈጠርን አላህ ከሁለቱ ወንዶችን ብቻ እርም አደረገን ወይንስ ሴቶችን ብቻ? ወይስ የሁለቱ ሴቶች ማህፀኖች ያጠቃለሉትን? በእውነቱ አላህ በዚህ ነገር ባዘዛችሁ ጊዜ በቦታው ነበራችሁን? ሰዎችን ያለ እውቀት ሊያጠም በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጠፈ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማን ነው? አላህ በደለኞችን ህዝቦች ቅኑን መንገድ አይመራም።

✶ የእንስሳዎች አፈጣጠር ብቻ በራሱ ለአላህ መኖርና ብቸኛ አምላክነት በቂ ማስረጃ ነው። እንስሳዎች ብዙ ተዐምራት እደሚታይባቸው «ግመል እንዴት እንደተፈጠረች አይመለከቱምን» በማለት አስታውሰናል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛም (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- ««አንድ እረኛ ከብቶቹን እየጠበቀ ሳለ አንድ ተኩላ መጥቶ በመካከላቸው አንዷን ይዞበት ሄደ። እረኛውም ተኩላውን እንዲመልስለት ጠየቀው። ተኩላው ዞር አለና «በዱር እንስሳት ቀን ከኔ ሌላ ማንም የሚጠብቃት ባይኖር ማን ጠባቂ ሊሆናት ነው?» አለው። እንዲሁ አንድ ሰው አንዲት ላም ጭነት ጭኖ እየተጓዘ ሳለ ላሚ ወደ ሰውየው ዞረችና «እኔ ለዚህ አይነቱ ስራ አልተፈጠርኩም። የተፈጠርኩት ለእርሻ ስራ ነው እንጂ» አለችው። ይህን ጊዜ ሰዎች «ሱብሓነ አላህ» አሉ። ነብዩም «እኔ፤ አቡበክርና ዑመር በዚህ እናምናለን» አሉ።

**ከቤት እንስሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (132-142) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ከዓለም የተብቃቃ፤ የታዛዥሮቹ ትዕዛዝም ሆነ የወንጀሎቹ ወንጀል በሱ ላይ ምንም ለውጥ እንዳማያመጣ፤
2. አላህ እንድንፈፅማቸው ያዘዛቸው ነገሮች ሁሉ በዱንያም በአኼራ ጠቀሜታቸው ለእኛ መሆኑን ነው፤

3. አላህ ቅጣት ሊያወርድበት የፈለገ ሰው ማንም ሊያድነው እንደማይችል፤
4. ነብዩ (ﷺ) ከሓዲያን በሚያደርሱባቸው ስቃይ የነበራቸው ፅናት፤
5. በአላህ ማጋራት የግፎች ሁሉ የበላይ ግፍ መሆኑን፤
6. ሴትን ከነህይወቷ መቅበር ሰይጣን የሰውን ልጅ ካሳሳተባቸው የመሀይማን ተግባራት አንዱ መሆኑን፤
7. ሙስሊሞች ሲያርዱ የአላህን ስም መጥራት እንዳለባቸውና ከእሱ ስም ሌላ ማውሳት ክልክል መሆኑን፤
8. መሀይማን በራሳቸው ላይ ያለ አንዳች መመሪያ ብዙ ነገሮች እርም እንዳደረጉ፤
9. መጋቢው አላህ ብቻ በመሆኑ ድህነትን ፈርቶ ልጅን መግደል እንደማይፈቀድ፤
10. በእኛ ላይ የዋላቸው የአላህ ፀጋዎች ቁጥር ስፍር የሌላቸው በመሆናቸው ልናመሰግነው እንደሚገባ፤
11. በሁሉም ነገር ላይ አባካኝነት የተከለከለ መሆኑን እንማራለን።

قُل لَّآ أَجِدُ فِي مَآ أُوحِيَ إِلَيَّ مُحَرَّمًا عَلَىٰ طَاعِمٍ يَطْعَمُهُۥٓ إِلَّآ أَن يَكُونَ مَيْتَةً أَوْ دَمًا
مَّسْفُوحًا أَوْ لَحْمَ خِنزِيرٍ فَإِنَّهُۥ رِجْسٌ أَوْ فِسْقًا أُهِلَّ لِغَيْرِ ٱللَّهِ بِهِۦ ۚ فَمَنِ ٱضْطُرَّ غَيْرَ بَاغٍ
وَلَا عَادٍ فَإِنَّ رَبَّكَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٤٥﴾

**145.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እኔ በተወረደው ቁርኣን ውስጥ በክት ወይም ፈሳሽ ደም፤ ወይም የአሳማ ስጋ እርሱ ርኩስ ነውና ወይም በአመፅ ከአላህ ስም ሌላ በእርሱ ላይ የተወሳበት ካልሆነ በስተቀር በሚመገበው ተመጋቢ ላይ እርም የሆነ ነገር አላገኝም በላቸው። አመፀኛና ወሰን ያለፈ ሳይሆን የተገደደ ሰው ከተወሱት ነገሮች ነፍስን የማዳን ያህል ቢበላ ኃጢአት የለበትም። ጌታህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

وَعَلَى ٱلَّذِينَ هَادُواْ حَرَّمْنَا كُلَّ ذِي ظُفُرٍ ۖ وَمِنَ ٱلْبَقَرِ وَٱلْغَنَمِ حَرَّمْنَا عَلَيْهِمْ شُحُومَهُمَآ إِلَّا مَا
حَمَلَتْ ظُهُورُهُمَآ أَوِ ٱلْحَوَايَآ أَوْ مَا ٱخْتَلَطَ بِعَظْمٍ ۚ ذَٰلِكَ جَزَيْنَٰهُم بِبَغْيِهِمْ ۖ وَإِنَّا لَصَٰدِقُونَ ﴿١٤٦﴾
فَإِن كَذَّبُوكَ فَقُل رَّبُّكُمْ ذُو رَحْمَةٍ وَٰسِعَةٍ وَلَا يُرَدُّ بَأْسُهُۥ عَنِ ٱلْقَوْمِ ٱلْمُجْرِمِينَ ﴿١٤٧﴾

**146-147.** በእነዚያም አይሁዳውያን በሆኑት ላይ የጥፍር ባለቤት እንስሳትን ሁሉ እርም አደረግንባቸው። ከከብት፤ ከፍየልና ከበግ ሞራዎቻቸውን፤ ጀርባዎቻቸው ወይም አንጀቶቻቸው የተሸከሙት ወይም በአጥንት የተቀላቀሉ ስብ ሲቀር በእነርሱ ላይ እርም አደረግን። በአመፃቸው ምክንያት ይህን በማድረግ ቀጣናቸው። እኛም እውነተኞች ነን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢያስተባብሉልህ፡- ጌታችሁ የሰፊ ችሮታ ባለቤት ነው። ብርቱ ቅጣቱም ከአመፀኞች ህዝቦች ላይ አይመለስም በላቸው።

سَيَقُولُ ٱلَّذِينَ أَشۡرَكُواْ لَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ مَآ أَشۡرَكۡنَا وَلَآ ءَابَآؤُنَا وَلَا حَرَّمۡنَا مِن شَيۡءٖۚ كَذَٰلِكَ كَذَّبَ
ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ حَتَّىٰ ذَاقُواْ بَأۡسَنَاۗ قُلۡ هَلۡ عِندَكُم مِّنۡ عِلۡمٖ فَتُخۡرِجُوهُ لَنَآۖ إِن تَتَّبِعُونَ
إِلَّا ٱلظَّنَّ وَإِنۡ أَنتُمۡ إِلَّا تَخۡرُصُونَ ﴿١٤٨﴾ قُلۡ فَلِلَّهِ ٱلۡحُجَّةُ ٱلۡبَٰلِغَةُۖ فَلَوۡ شَآءَ لَهَدَىٰكُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿١٤٩﴾

**148-149.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ ያጋሩ ሰዎች ሁሉ አላህ በሻ ኖሮ እኛም ሆነ አባቶቻችን በአላህ ባላጋራንና አንዳችንም ነገር እርም ባላደረግን ነበር ይላሉ፡፡ ልክ እነዚህ እንደ አስተባበሉህ ሁሉ እነዚያ ከበፊታቸው የነበሩ ሕዝቦችም ብርቱ ቅጣታችንን እስከ ቀመሱ ድረስ አስተባበሉ፡፡ ለእኛ ታስተምሩን ዘንድ (ማጋራታችሁን ለመውደድ) እናንተ ዘንድ እውቀት አለን? ጥርጣሬን እንጂ ሌላ አትከተሉም፡፡ እናንተ ዋሾዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም በላቸው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የተሟላው ማስረጃ የአላህ ማስረጃ ብቻ ነው፡፡ በፈለገ ኖሮ ሁላችሁንም ባቀናችሁ ነበር በላቸው፡፡

قُلۡ هَلُمَّ شُهَدَآءَكُمُ ٱلَّذِينَ يَشۡهَدُونَ أَنَّ ٱللَّهَ حَرَّمَ هَٰذَاۖ فَإِن شَهِدُواْ فَلَا تَشۡهَدۡ مَعَهُمۡۚ
وَلَا تَتَّبِعۡ أَهۡوَآءَ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِ وَهُم بِرَبِّهِمۡ يَعۡدِلُونَ ﴿١٥٠﴾
۞قُلۡ تَعَالَوۡاْ أَتۡلُ مَا حَرَّمَ رَبُّكُمۡ عَلَيۡكُمۡۖ أَلَّا تُشۡرِكُواْ بِهِۦ شَيۡـٔٗاۖ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنٗاۖ وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ
أَوۡلَٰدَكُم مِّنۡ إِمۡلَٰقٖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكُمۡ وَإِيَّاهُمۡۖ وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَۖ
وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ ذَٰلِكُمۡ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ﴿١٥١﴾

**150-151.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን አላህ ዘንድ እርም ማድረጉን የሚመሰክሩትን ምስክሮቻችሁን እስቲ አምጡ በላቸው፡፡ ቢመሰክሩም ከእነርሱ ጋር አትመስክር፡፡ የእነዚያንም በአንቀፆቻችን ያስተባበሉትን የእነዚያንም እነርሱ በጌታቸው ሌላን የሚያስተካክሉ ሲሆኑ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑትን ሰዎች ዝንባሌዎች አትከተል፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኑ ወደ ጌታችሁ በእናንተ ላይ እርም ያደረገውን ነገርና በእርሱም ያዘዛችሁን ላንብብላችሁ በላቸው፡፡ እርሱም በአላህ ምንንም ነገር አታጋሩ፡፡ ለወላጆቻችሁም በጎ ስራን ስሩ፡፡ ልጆቻችሁንም ድህነትን ፈርታችሁ አትግደሉ፡፡ እኛ እናንተንም ሆነ እነርሱን እንመግባችኋለንና፡፡ መጥፎ ስራ የተገለፀውንም ሆነ የተደበቀውን ሁሉ አትቅረቡ፡፡ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ በህግ ቢሆን እንጂ አትግደሉ፡፡ ይህን ታውቁ ዘንድ (አላህ) በእርሱ አዘዛችሁ፡፡

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (143-151) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. በጃሂልያ ዘመን ይሰሩ የነበሩ ብዙ መጥፎ ነገሮችን ኢስላም እንዳረመ፤
2. ከአላህ ላይ ከቀጠፈ ሰው የበለጠ ግፈኛ እንደሌለ፤
3. አላህ እርም ያደረጋቸው ነገሮች ሁሉ ለሰዎ ልጆች ጉዳት የሚያደርሱ እንደሆኑ፤
4. ከሓዲያን ክርክራቸው ሁልጊዜም በሀሰት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ፤
5. የሽርክ አይነቶች ሁሉ እርም እንደሆኑ፤
6. ለወላጆች መልካም መዋል ግዴታ እንደሆነ፤
7. የሰውን ነፍስ ማጥፋትና ሰዎችን መበደል ወንጀል መሆኑን እንማራለን።

وَلَا تَقْرَبُوا۟ مَالَ ٱلْيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِى هِىَ أَحْسَنُ حَتَّىٰ يَبْلُغَ أَشُدَّهُۥ ۖ وَأَوْفُوا۟ ٱلْكَيْلَ وَٱلْمِيزَانَ
بِٱلْقِسْطِ ۖ لَا نُكَلِّفُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَا ۖ وَإِذَا قُلْتُمْ فَٱعْدِلُوا۟ وَلَوْ كَانَ ذَا قُرْبَىٰ ۖ وَبِعَهْدِ ٱللَّهِ
أَوْفُوا۟ ۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ ﴿١٥٢﴾ وَأَنَّ هَٰذَا صِرَٰطِى مُسْتَقِيمًا فَٱتَّبِعُوهُ ۖ
وَلَا تَتَّبِعُوا۟ ٱلسُّبُلَ فَتَفَرَّقَ بِكُمْ عَن سَبِيلِهِۦ ۚ ذَٰلِكُمْ وَصَّىٰكُم بِهِۦ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٥٣﴾

**152-153.** (ሙስሊሞች ሆይ!) የየቲምን ገንዘብ አካለ መጠን እስኪድረስ ድረስ በዚያች እርሷ በመልካም ሁኔታ እንጂ አትቅረቡ። ስፍርንና ሚዛንንም በትክክል ሙሉ። ማንኛዋም ነፍስ የችሎታዋን ያህል እንጂ አናስገድድም። በተናገራችሁ ጊዜ በዘመዶቻችሁ ላይ ቢሆንም እንኳ እውነትን በመናገር አስተካክሉ። በአላህ ቃል ኪዳን ሙሉ። ይህን ትገሰጹ ዘንድ አላህ በእርሱ አዘዛችሁ። ይህ ቀጥተኛው መንገዴ ነው። እናም እርሱን ብቻ ተከተሉ። የተለያዩ የጥመት መንገዶችንም አትከተሉ። ከቀጥተኛው መንገድ እናንተን ይለያይዋችኋልና። ይህን ትጠነቀቁ ዘንድ አላህ በእርሱ አዘዛችሁ።

ثُمَّ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ تَمَامًا عَلَى ٱلَّذِىٓ أَحْسَنَ وَتَفْصِيلًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً
لَّعَلَّهُم بِلِقَآءِ رَبِّهِمْ يُؤْمِنُونَ ﴿١٥٤﴾

**154.** ከዚያም ለሙሳ መልካም በሰራው ላይ ፀጋችንን ለማሟላት ነገርንም ሁሉ ለመዘርዘር መጽሐፍን ለኢስራኤል ልጆች መሪና እዝነት ይሆን ዘንድ ሰጠናቸው። እነርሱ ከጌታቸው በመገናኘት ጉዳይ ሊያምኑ ይከጀላልና።

وَهَٰذَا كِتَٰبٌ أَنزَلْنَٰهُ مُبَارَكٌ فَٱتَّبِعُوهُ وَٱتَّقُوا۟ لَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ﴿١٥٥﴾

**155.** ይህ ያወረድነው የሆነ የተባረከ መጽሐፍ ነው። እናም ተከተሉት ይታዘንላችሁ ዘንድ ከክህደት ተጠንቀቁ።

أَن تَقُولُوٓاْ إِنَّمَآ أُنزِلَ ٱلۡكِتَٰبُ عَلَىٰ طَآئِفَتَيۡنِ مِن قَبۡلِنَا وَإِن كُنَّا عَن دِرَاسَتِهِمۡ لَغَٰفِلِينَ ﴿١٥٦﴾
أَوۡ تَقُولُواْ لَوۡ أَنَّآ أُنزِلَ عَلَيۡنَا ٱلۡكِتَٰبُ لَكُنَّآ أَهۡدَىٰ مِنۡهُمۡۚ فَقَدۡ جَآءَكُم بَيِّنَةٞ مِّن رَّبِّكُمۡ
وَهُدٗى وَرَحۡمَةٞۚ فَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّن كَذَّبَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَصَدَفَ عَنۡهَاۗ سَنَجۡزِي ٱلَّذِينَ يَصۡدِفُونَ
عَنۡ ءَايَٰتِنَا سُوٓءَ ٱلۡعَذَابِ بِمَا كَانُواْ يَصۡدِفُونَ ﴿١٥٧﴾

**156-157.** ያወረድነውንም መጽሐፍ የተወረደው ከፊታችን በነበሩ ሁለቱ ህዝቦች ላይ ብቻ ነው። እኛም ከንባባቸው ዘንጊዎች ነበርን እንዳትሉ ነው። ወይም እኛ መጽሐፍ በእኛ ላይ በተወረደ ኖሮ ከእነርሱ ይበልጥ የተመራን እንሆን ነበር እንዳትሉ ነው። ስለዚህ ከጌታችሁ ግልፅ ማስረጃ፣ መመሪያ እና እዝነት በእርግጥ መጣላችሁ። በአላህ አንቀፆች ካስተባበለና ከእነርሱም ከዞረ ሰው ይበልጥ ራሱን በዳይ ማን ነው? እነዚያን አንቀፆችን የሚተውትን ይተውት በነበሩት ምክንያት ብርቱ ቅጣት በእርግጥ እንቀጣቸዋለን።

هَلۡ يَنظُرُونَ إِلَّآ أَن تَأۡتِيَهُمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ أَوۡ يَأۡتِيَ رَبُّكَ أَوۡ يَأۡتِيَ بَعۡضُ ءَايَٰتِ رَبِّكَۗ
يَوۡمَ يَأۡتِي بَعۡضُ ءَايَٰتِ رَبِّكَ لَا يَنفَعُ نَفۡسًا إِيمَٰنُهَا لَمۡ تَكُنۡ ءَامَنَتۡ مِن قَبۡلُ
أَوۡ كَسَبَتۡ فِيٓ إِيمَٰنِهَا خَيۡرٗاۗ قُلِ ٱنتَظِرُوٓاْ إِنَّا مُنتَظِرُونَ ﴿١٥٨﴾

**158.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲያን መላዕክት ልትመጣላቸው ወይንም ጌታህ ሊመጣ ወይም ከጌታህ ምልክቶች ከፊሉ ሊመጣ እንጂ ሌላን ይጠባበቃሉን? ከጌታህ ምልክቶች ከፊሉ የሚመጣበት ቀን ግን ከዚያ በፊት አማኝ ያልነበረች ነፍስ እምነቷ ወይም አምና በእምነቷ በጎ ያልሰራች ነፍስ ሁሉ ፀፀቷ አይጠቅማትም*። ያን ቀን እናንተም ተጠባበቁ እኛም ተጠባባቂዎች ነን በላቸው።

✷ ይህ አባባል ወደ አላህ ንስሃ መግባት የሚጠቅመው የትንሳኤ ቀን ምልክቶች ከመከሰታቸው በፊት መሆኑን ነው የሚያመለክተን። ስለዚሁ ጉዳይ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ ብለዋል፦ «ፀሐይ ከምዕራብ እስከምትወጣ ድረስ የመጨረሻ ቀን አይከሰትም። ሰዎችም ይህን ክስተት ይመለከታሉ። በዚህ ወቅትም በምድር ላይ በሕይወት የሚኖር ሁሉ እምነት ይኖረዋል። ይህም «ከጌታህ ምልክቶች ከፊሉ በሚመጣ ቀን ከዚያ በፊት አማኝ ያልሆነች ነፍስ እምነቷ ወይም በእምነቷ ጊዜ በጎ ያልሰራች ነፍስ ፅዳትዋ አይጠቅማትም....» (አል-አንዓም፡ 158)

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «እነዚህ ሶስት ምልክቶች በሚከሰቱበት ጊዜ ቀድሞውኑ ያላመነ ሰው የሚያደርገው ጥሩ እምነት ምንም አይጠቅመውም። እርሱም፦

1. የፀሐይ ከምዕራብ አቅጣጫ መውጣት፤
2. የመሲሕ አድ. ደጃል መምጣት፤
3. ከመሬት ውስጥ ያለው እንስሳ መውጣት።» (ሙስሊም ዘግበውታል)

إِنَّ ٱلَّذِينَ فَرَّقُواْ دِينَهُمْ وَكَانُواْ شِيَعًا لَّسْتَ مِنْهُمْ فِى شَىْءٍ ۚ إِنَّمَآ أَمْرُهُمْ إِلَى ٱللَّهِ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا كَانُواْ يَفْعَلُونَ ﴿١٥٩﴾

**159.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነዚያ ሃይማኖታቸውን ከለያዩና ቡድን ቡድን ከሆኑ ሰዎች ጋር አይደለህም፡፡ ነገራቸው ወደ አላህ ብቻ ነው፡፡ ከዚያ ይሰሩት የነበሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡

مَن جَآءَ بِٱلْحَسَنَةِ فَلَهُۥ عَشْرُ أَمْثَالِهَا ۖ وَمَن جَآءَ بِٱلسَّيِّئَةِ فَلَا يُجْزَىٰٓ إِلَّا مِثْلَهَا وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿١٦٠﴾

**160.** መልካምን ስራ የሰራ ሰው ሁሉ ለእርሱ አስር እጥፍ ምንዳ አሉት፡፡ ክፉ ስራን የሰራ ሰው ግን መሰሏን ብቻ እንጂ አይመነዳም፡፡ እነርሱም ቅንጣት አይበደሉም፡፡

قُلْ إِنَّنِى هَدَىٰنِى رَبِّىٓ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ دِينًا قِيَمًا مِّلَّةَ إِبْرَٰهِيمَ حَنِيفًا ۚ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٦١﴾ قُلْ إِنَّ صَلَاتِى وَنُسُكِى وَمَحْيَاىَ وَمَمَاتِى لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٦٢﴾ لَا شَرِيكَ لَهُۥ ۖ وَبِذَٰلِكَ أُمِرْتُ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلْمُسْلِمِينَ ﴿١٦٣﴾

**161-163.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ ጌታዬ ወደ ቀጥተኛው መንገድ ትክክለኛ ሀይማኖት ወደ እውነት አዘንባይ ሲሆን የአብርሃምን መንገድ መራኝ፡፡ እሱም ከአጋሪዎች አልነበረም በል፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስግደቴ፣ መገዛቴ፣ መስዋዕቴ፣ ሕይወቴ፣ ሞቴ የሚገባው ለዓለማት ጌታ ለአላህ ብቻ ነው በል፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በምንም ነገር እርሱ ተጋሪ የለውም፡፡ አላህን ከተጋሪ በማጥራት ታዘዝኩ፡፡ እኔም የሙስሊሞች መጀመሪያ ሰው ነኝ በል፡፡

قُلْ أَغَيْرَ ٱللَّهِ أَبْغِى رَبًّا وَهُوَ رَبُّ كُلِّ شَىْءٍ ۚ وَلَا تَكْسِبُ كُلُّ نَفْسٍ إِلَّا عَلَيْهَا ۚ وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزْرَ أُخْرَىٰ ۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُم مَّرْجِعُكُمْ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ فِيهِ تَخْتَلِفُونَ ﴿١٦٤﴾

**164.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱ (አላህ) የሁሉ ጌታ ሲሆን ከአላህ በቀር ሌላን ጌታ እፈልጋለሁን? ነፍስ ሁሉ በራሷ ላይ እንጂ ክፉን አትሰራም፡፡ ወንጀለኛ ነፍስ ሁሉ የሌላይቱን ነፍስ ኃጢአት አትሸከምም፡፡ ከዚያ መመለሻችሁ ወደ ጌታችሁ ነው፡፡ ከዚያ በዚህ ዓለም ትለያዩበት የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል በላቸው፡፡

وَهُوَ ٱلَّذِى جَعَلَكُمْ خَلَٰٓئِفَ ٱلْأَرْضِ وَرَفَعَ بَعْضَكُمْ فَوْقَ بَعْضٍ دَرَجَٰتٍ لِّيَبْلُوَكُمْ فِى مَآ ءَاتَىٰكُمْ ۗ إِنَّ رَبَّكَ سَرِيعُ ٱلْعِقَابِ وَإِنَّهُۥ لَغَفُورٌ رَّحِيمٌۢ ١٦٥

**165.** (ሰዎች ሆይ)፣ እርሱ (አላህ) ያ፣ በምድር ላይ ምትኮች ያደረጋችሁ በሰጣችሁም ፀጋ ሊፈትናችሁ ከፊላችሁን በከፊሉ ላይ በደረጃዎች ከፍ ያደረገ ሃያል ጌታ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ቅጣቱ ፈጣን ነው። አላህ እጅግ መሀሪና ሩህሩህ ነው።

**ከቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (152-165) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ:-**

1. ኢስላም የቲምን በመንከባከብና በንብረቱ ጉዳይ ላይ ምን ያህል ትኩረት እንደሰጠ፤
2. የሰዎችን መብት በመጠበቅና ፍትህን በማስከበር ኢስላም ያለው አቋም፤
3. ለአላህም ሆነ ለሰዎች የተገባን ቃል ማክበር ግዴታ መሆኑን፤
4. ነብያት ያስተማሩት የአላህ ሃይማኖት አንድ ብቻ እንደሆነ፤
5. የነብዩ ኢብራሂም መንገድ ትክክለኛ ሃይማኖት እንደሆነ ኢስላም ስለ ማስተማሩ፤
6. ሶላትም ሆነ ሌላ የአምልኮት ተግባራትን ስንፈፅም ለአንድ አላህ ብቻ ብለን መፈፀም እዳለብን፤
7. አላህ ጎጂም ጠቃሚም ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል መሆኑን ማመን እንዳለብን፤
8. የሰው ልጅ እራሱ በሰራው የሚጠየቅና እንደተግባሩ ዋጋውን የሚያገኝ ሲሆን ማንም ሰው በሌላ ሰው ወንጀል የማይጠየቅ መሆኑን፤
9. አላህ ሰዎችን በሀብት፤ በድህነት፤ በደግ ነገር፤ በመጥፎ ነገር የፈተነ መሆኑንና እድለኛ ማለት ይህችን ዓለም በትክክለኛ እምነትና በመልካም ስራ ያሳለፈ ብቻ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የቤት እንሰሳዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (7)
# የአዕራፍ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-አዕራፍ)

سُورَةُ الأَعْرَافِ

### የወረደው በመካ ነው። የምዕራፉ አናቅፅ (206) ናቸው።
### የሱረቱ አል አዕራፍ መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በመካ ከወረዱ ረጃጅም ምእራፎች አንዱ ነው። መልዕክቱም እንደሌሎቹ የመካ ምእራፎች ሁሉ እምነትን፤ የነብያት ታሪክን፤ በሽርክና በተውሂድ መካከል ያለውን ግልጽ ልዩነትና በተውሂድ ላይ በየጊዜው የተከፈለውን መስዋዕትነት ይዘረዝራል። ሐቅ አሸናፊነቱ አይቀሬ መሆኑንም ያበስራል። የቁርኣንን ትልቅነትና አላህ ለሰው ልጆች የዋለላቸውን ከፍተኛ ውለታዎችንም በመጠኑ ይቃኛል። የአደምንና የሰይጣንን አስገራሚ ታሪክ ከመነሻው እስከ መጨረሻው ምን እንደሚመስል፤ ሰይጣን ለሰው ልጆች ያለውን ጠላትነትና የሰው ልጆች ከሰይጣን ተንኮል ነጻ ለመሆን የሚያስፈልጋቸው በአላህ ብቻ መመካት መሆኑን ያስተምራል። የተውሂድን ሀቅነት በማጽደቅ መልክቱን ይደመድማል። የዚህ ሱራ መግቢያ ከእሱረቱል-አንዓም ማጠቃለያ ጋር በጥብቅ የተያያዘ መልዕክት አለው።

የሰው አፈጣጠር እንዴት እንደነበር፤ ሐዋና አደም እንዴት እንደተፈጠሩ፤ ከጀነት እንዴት እንደወጡ፤ ሰይጣን ሰዎችን ሁልጊዜም ከመጎትጎት (በልብስም ሆነ በምግብ) እንደማያርፍ ያነሳና እንደሌሎች ሱራዎች በሰማይና በምድር አፈጣጠር ዙሪያ እንድንመራመር ይመክራል። ከዚያ በኋላ ከኑህ በመጀመር የብዙ ነብያትን ታሪክ ይዘረዝራል። በስተመጨረሻ ስለዚያ ሂዳያን ከአላህ ተችሮት ሰይጣን ስላሳሳተው ሰው ታሪክ አውስቶ ነብዩ (ﷺ) ወዳስተማሩት ብቸኛ ሐቅ ጥሪ በማድረግ አስተምህሮቱን ይደመድማል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

الٓمٓصٓ ١

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም፤ ሷድ።* (አላህ በእነዚህ ፊደላት ምን እንደፈለገ ራሱ ብቻ ያውቃል።)

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

كِتَٰبٌ أُنزِلَ إِلَيۡكَ فَلَا يَكُن فِي صَدۡرِكَ حَرَجٞ مِّنۡهُ لِتُنذِرَ بِهِۦ وَذِكۡرَىٰ لِلۡمُؤۡمِنِينَ ٢
ٱتَّبِعُواْ مَآ أُنزِلَ إِلَيۡكُم مِّن رَّبِّكُمۡ وَلَا تَتَّبِعُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَۗ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ ٣

**2-3.** (መልዕተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፤ ይህ ወደ አንተ የተወረደ ቁርኣን ነው። ስለዚህ ልብህ ውስጥ ከእርሱ ጭንቀት አይኑር። የተወረደውም በእርሱ ከሓዲያንን ልታስፈራራበትና ለምዕመናን መገሰጫ እንዲሆን ነው። ሰዎች ሆይ፤ ከጌታችሁ ወደ እናንተ የተወረደላችሁን መልዕክት ተከተሉ። ከአላህም ሌላ ረዳቶችን አትከተሉ። ጥቂትን ብቻ ትገሰፃላችሁ።

وَكَم مِّن قَرۡيَةٍ أَهۡلَكۡنَٰهَا فَجَآءَهَا بَأۡسُنَا بَيَٰتًا أَوۡ هُمۡ قَآئِلُونَ ٤
فَمَا كَانَ دَعۡوَىٰهُمۡ إِذۡ جَآءَهُم بَأۡسُنَآ إِلَّآ أَن قَالُوٓاْ إِنَّا كُنَّا ظَٰلِمِينَ ٥

**4-5.** ከከተማ ሰዎች መካከል ልናጠፋቸው የፈለግነውን ወዲያውኑ ብርቱ ቅጣታችን ሌሊት ወይም ቀን እነርሱ በቀትር አርፈው ሳሉ የመጣባቸው ብዙ ህዝቦች ናቸው። ቅጣታችንም በመጣባቸው ጊዜ ፀሎታቸው እኛ በደለኞች ነበርን ከማለት በቀር ሌላ አልነበረም።

فَلَنَسۡـَٔلَنَّ ٱلَّذِينَ أُرۡسِلَ إِلَيۡهِمۡ وَلَنَسۡـَٔلَنَّ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ٦
فَلَنَقُصَّنَّ عَلَيۡهِم بِعِلۡمٖۖ وَمَا كُنَّا غَآئِبِينَ ٧

**6-7.** እነዚያንም ወደ እነርሱ የተላከባቸውን ህዝቦችና መልዕክተኞችን እንጠይቃቸዋለን። ከዚያ በእነርሱ ላይ የነበሩትን ሁሉ ከእውቀት ጋር በእርግጥ እንተርክላቸዋለን። የራቅን አልነበርንምና።

وَٱلۡوَزۡنُ يَوۡمَئِذٍ ٱلۡحَقُّۚ فَمَن ثَقُلَتۡ مَوَٰزِينُهُۥ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ﴿٨﴾
وَمَنۡ خَفَّتۡ مَوَٰزِينُهُۥ فَأُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓاْ أَنفُسَهُم بِمَا كَانُواْ بِـَٔايَٰتِنَا يَظۡلِمُونَ ﴿٩﴾

**8-9.** ትክክለኛው ሚዛን ማለት የዚያን ቀኑ ሚዛን ብቻ ነው።* እናም እነዚያ ሚዛኖቻቸው የከበዱላቸው ሰዎችም እነርሱ የፈለጉትን ያገኙ እነርሱ ብቻ ናቸው። እነዚያ ሚዛኖቻቸው የቀለሉባቸው ሰዎች እነዚያ እነርሱ በአንቀፆቻችን ይክዱ በነበሩት ምክንያት ነፍሶቻቸውን እነርሱ ብቻ ያከሰሩ ናቸው።

* ይህ ቀን በጣም አስፈሪው ቀን ነው። አንዱ ለሌላው ምንንም አይሰጥም አያበድርም። ሰዎች በዚህ ዐለም ሲኖሩ ለሰሩት ተግባር ሁሉ ተገቢ ምንዳቸውን እንዲያገኙ በእውነተኛና አስተማማኝ በሆነ ሁለት ሳህን ባለው ሚዛን የሰዎች ተግባር ይመዘናል። ለአላህ ንፁህ የሆንና ሸሪዓውን ገጥሞ የተፈፀመ ተግባር ሁሉ ሚዛኑን ያከብደዋል። ለምሳሌ ላኢላሀ ኢለሏህ ማለት፤ መልካም ስነ ምግባር፤ አልሐምዱሊለህ፤ ሱብሃነአላህ ወቢሐምዲህ፤ ሱብሓነሏህልዐዚም የሚለውን ዚክር ይመስል። ሰዎች በመልካም ተግባራቸውም ይመነዳሉ። የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «እጅግ በጣም ሩህሩህ በሆነው ጌታ ዘንድ እጅጉን የተወደዱ፤ ለአንደበት እጅግ የቀለሉ፤ ሚዛን ላይ ደግሞ በጣም ከባድ የሆኑ ሁለት ቃላቶች አሉ። ሱብሐን አላህ ወቢሀምዲሂ ሱብሐን አላህ አል አዚም።

وَلَقَدۡ مَكَّنَّٰكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَجَعَلۡنَا لَكُمۡ فِيهَا مَعَٰيِشَۗ قَلِيلٗا مَّا تَشۡكُرُونَ ﴿١٠﴾

**10.** (ሰዎች ሆይ!) በምድር ላይ በእርግጥም አስመቸናችሁ። በእርሷም ላይ ለእናንተ መኖሪያዎችን አደረግንላችሁ ምስጋናችሁ በጣም ጥቂት ነው።

وَلَقَدۡ خَلَقۡنَٰكُمۡ ثُمَّ صَوَّرۡنَٰكُمۡ ثُمَّ قُلۡنَا لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ
فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ لَمۡ يَكُن مِّنَ ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿١١﴾

**11.** (ሰዎች ሆይ)፣ በእርግጥም ፈጠርናችሁ። ከዚያም ቀረጽናችሁ። ከዚያም ለመላዕክት ሁላችሁም ለአዳም ስገዱ አልን። ወዲያውም ሁሉም ሰገዱ። ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ሲቀር። እሱማ ከሰጋጆቹ አልሆነም።

قَالَ مَا مَنَعَكَ أَلَّا تَسۡجُدَ إِذۡ أَمَرۡتُكَۖ قَالَ أَنَا۠ خَيۡرٞ مِّنۡهُ خَلَقۡتَنِي مِن نَّارٖ وَخَلَقۡتَهُۥ
مِن طِينٖ ﴿١٢﴾ قَالَ فَٱهۡبِطۡ مِنۡهَا فَمَا يَكُونُ لَكَ أَن تَتَكَبَّرَ فِيهَا فَٱخۡرُجۡ إِنَّكَ مِنَ
ٱلصَّٰغِرِينَ ﴿١٣﴾ قَالَ أَنظِرۡنِيٓ إِلَىٰ يَوۡمِ يُبۡعَثُونَ ﴿١٤﴾ قَالَ إِنَّكَ مِنَ ٱلۡمُنظَرِينَ ﴿١٥﴾ قَالَ فَبِمَآ
أَغۡوَيۡتَنِي لَأَقۡعُدَنَّ لَهُمۡ صِرَٰطَكَ ٱلۡمُسۡتَقِيمَ ﴿١٦﴾ ثُمَّ لَأٓتِيَنَّهُم مِّنۢ بَيۡنِ أَيۡدِيهِمۡ وَمِنۡ خَلۡفِهِمۡ
وَعَنۡ أَيۡمَٰنِهِمۡ وَعَن شَمَآئِلِهِمۡۖ وَلَا تَجِدُ أَكۡثَرَهُمۡ شَٰكِرِينَ ﴿١٧﴾ قَالَ ٱخۡرُجۡ مِنۡهَا مَذۡءُومٗا
مَّدۡحُورٗاۖ لَّمَن تَبِعَكَ مِنۡهُمۡ لَأَمۡلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿١٨﴾

**12-18.** አላህም (ኢብሊስ ሆይ)፣ ባዘዝኩህ ጊዜ ከመስገድ ምን ከለከለህ? አለው። (ኢብሊስም) እኔ ከእርሱ የበለጥኩ ነኝ። እኔን ከእሳት ፈጠርከኝ እርሱን ግን ከጭቃ ፈጠርከው አለ። ከእርሷ ውረድ። በእርሷ ውስጥ ልትኮራ አይገባህምና። ውጣም። አንተ ከወራዶቹ አንዱ ነህና አለው። (ኢብሊስ) እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ አለ። አላህ አንተ ከሚቆዩት ነህ አለው። ስላጠመምከኝም ለእነርሱ በቀጥተኛው መንገድ ላይ በእርግጥ እቀመጥባቸዋለሁ አለ። ከዚያም ከበስተፊቶቻቸው፣ ከኋላቸውም፣ ከቀኞቻቸውና ከግራዎቻቸውም በእርግጥ እመጣባቸዋለሁ። አብዛኞቻቸውንም አመስጋኞች ሆነው አታገኛቸውም (አለ)። የተጠላህ ብራሪ ስትሆን ከእርሷ ውጣ። ከእነርሱ መካከልም አንተን ከተከተለህ ከናንተ ከሁላችሁም ገሀነምን በእርግጥም በእናንተ እሞላታለሁ አለው።

وَيَـٰٓـَٔادَمُ ٱسۡكُنۡ أَنتَ وَزَوۡجُكَ ٱلۡجَنَّةَ فَكُلَا مِنۡ حَيۡثُ شِئۡتُمَا
وَلَا تَقۡرَبَا هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةَ فَتَكُونَا مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٩

**19.** አደም ሆይ፣ አንተም ሚስትህም በገነት ተቀመጡ። ከፈለጋችሁትም አይነት በፈለጋችሁት ስፍራ ብሉ። ግን ይህችን ዛፍ አትቅረቡ። ራሳቸውን ከሚበድሉት ትሆናላችሁና (አላቸው)።

فَوَسۡوَسَ لَهُمَا ٱلشَّيۡطَٰنُ لِيُبۡدِيَ لَهُمَا مَا وُۥرِيَ عَنۡهُمَا مِن سَوۡءَٰتِهِمَا وَقَالَ مَا نَهَىٰكُمَا
رَبُّكُمَا عَنۡ هَٰذِهِ ٱلشَّجَرَةِ إِلَّآ أَن تَكُونَا مَلَكَيۡنِ أَوۡ تَكُونَا مِنَ ٱلۡخَٰلِدِينَ ٢٠
وَقَاسَمَهُمَآ إِنِّي لَكُمَا لَمِنَ ٱلنَّٰصِحِينَ ٢١ فَدَلَّىٰهُمَا بِغُرُورٖۚ فَلَمَّا ذَاقَا ٱلشَّجَرَةَ بَدَتۡ لَهُمَا
سَوۡءَٰتُهُمَا وَطَفِقَا يَخۡصِفَانِ عَلَيۡهِمَا مِن وَرَقِ ٱلۡجَنَّةِۖ وَنَادَىٰهُمَا رَبُّهُمَآ أَلَمۡ أَنۡهَكُمَا عَن
تِلۡكُمَا ٱلشَّجَرَةِ وَأَقُل لَّكُمَآ إِنَّ ٱلشَّيۡطَٰنَ لَكُمَا عَدُوّٞ مُّبِينٞ ٢٢

**20-22.** ሰይጣንም ከሀፍረተ ገላቸው የተሸሸገውን ሊገልጽባቸው በድብቅ ንግግር ጎተጎታቸው። ጌታችሁ እኮ መልአኮች እንዳትሆኑ ወይም ከዘላለም ኗዋሪዎቹ እንዳትሆኑ እንጂ ከዚህች ዛፍ አልከለከልኳችሁም አላቸው። እኔ ለእናንተ በእርግጥ ከሚመክሯችሁ ነኝ ሲልም ማለላቸው። በማታለልም አዋረዳቸው። ከዛፊቱም በቀመሱ ጊዜ ሀፍረተ ገላቸው የሁለቱም ተገለጠባቸው። ከገነት ቅጠልም በላያቸው ላይ ይደርቱ ጀመር። ጌታቸውም ይህችን ዛፍ አልከለከልኳችሁም ነበርን? ሰይጣንም ለእናንተ ግልጽ ጠላት ነው አላልኳችሁም ነበርን? ሲል ጠራቸው።

**ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (1-22) ከሚገኙ አንኳር ነጥቦችመካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩ ሕዝቡን ያስተምሩ የነበረው ቁርአንን መሠረት አድርገው እንደነበር፤
2. ከአላህ የወረደውን ቁርኣንን እንጂ ስሜትን መከተል አግባብ አለመሆኑን፤
3. ያለፉት ሕዝቦች በጥፋታቸው ካጋጠማቸው ኪሳራ ትምህርት መውሰድ ተመሳሳይ አደጋ ላይ ላለመውደቅ መማሩ ተገቢ መሆኑን፤
4. ለመሞት በማጣጣር ላይ ወይም ቅጣትን በማየት ላይ ያሉ ሰዎች ተውባህ (ንስሃ) መግባታቸው ተቀባይነት እንደሌለው፤
5. በትንሳኤ እለት ከየተቀበርንበት ተቀስቅሰን ለጥያቄ እንደምንቀርብና የሥራችንን ውጤት እንደምንቀበል፤ በምድር ላይ ያከናወናቸው ተግባራት ሚዛን ላይ እንደሚቀመጡ፤
6. በትንሳኤ እለት ስለምድራዊ ተግባሮቻቸው የሚጠየቁት ተራ ሕዝቦች ብቻ ሳይሆኑ የአላህ ምርጥ አገልጋይ የሆኑት ነብያት ጭምር መሆናቸው የቀኑን ክብደት እንደሚያሳይ፤
7. በቂያማ እለት ደስታን ማግኘትም ሆነ ቅጣትን መከናነብ የሚኖረው የሰው ልጅ በዚህች ዓለም ቆይታው በሰራው ስራ ልክ እንደሚሆን፤
8. አላህ ለባሪያው በሰጠው ፀጋ ሊመሠገን እንደሚገባ፤
9. ኩራት ለሰው ልጅ የማይገባ አደገኛና ብልሹ ሥነ ምግባር ስለመሆኑ፤
10. እርግጠኛ ለመሆንና የተሳሳተ ግምት ሊያመጣ የሚችል ጉጉት በጣም የከፋ መሆኑን፤
11. ሰይጣንና የእርሱ ዘር ማንዘሮች የሰው ልጅን ከእምነት ወደ ክህደት በማውጣት ረገድ እጅግ አደገኛ የሆነ ሚና እንዳላቸው፤
12. አላህን ማመስገን ማለት በእርሱ ላይ ሙሉ እምነት በማሳደር መታዘዝ፤ በአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ማመንና መታዘዝ መሆኑን፤
13. ሰይጣን የአደምን ዘር የሚያሳስትበት ዋናው ዘዴ መጥፎ ነገሮችን በማስዋብ ለሰው ስሜት ቀስቃሽ አድርጎ በማቅረብ መሆኑን፤
14. ሰይጣን የሰው ልጆችን በሙሉ ከጥሩው ጎዳና አውጥቶ ወደ ተሳሳተው መንገድ ለመወርወር የሚፈልግ ግልፅ ጠላት መሆኑን፤
15. ለወንድም ሆነ ለሴት ሃፍረተ ገላን መሸፈን ኢስላማዊ ግዴታ መሆኑን፤
16. በአላህ መማል የተፈቀደ ከመሆኑ ጋር መህላ ለእውነት እንጂ ለሀሰት የማይፈቀድ መሆኑን እንረዳለን።

قَالَا رَبَّنَا ظَلَمۡنَآ أَنفُسَنَا وَإِن لَّمۡ تَغۡفِرۡ لَنَا وَتَرۡحَمۡنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ﴿٢٣﴾
قَالَ ٱهۡبِطُواْ بَعۡضُكُمۡ لِبَعۡضٍ عَدُوّٞۖ وَلَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ مُسۡتَقَرّٞ وَمَتَٰعٌ إِلَىٰ حِينٖ ﴿٢٤﴾
قَالَ فِيهَا تَحۡيَوۡنَ وَفِيهَا تَمُوتُونَ وَمِنۡهَا تُخۡرَجُونَ ﴿٢٥﴾

**23-25.** ጌታችን ሆይ፣ ነፍሶቻችንን በደልን። ለእኛ ባትምረንና ባታዝንልን በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን አሉ። አላህ ከፊላችሁ ለከፊሉ ጠላት ሲሆን ወደ ምድር ውረዱ። ለእናንተም በምድር ላይ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ መርጊያና መጠቀሚያ አላችሁ አላቸው። በእርሷ ላይ ትኖራላችሁ። በእርሷም ላይ ትሞታላችሁ። ከእርሷም ውስጥ ትወጣላችሁ አላቸው።

يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ قَدۡ أَنزَلۡنَا عَلَيۡكُمۡ لِبَاسٗا يُوَٰرِي سَوۡءَٰتِكُمۡ وَرِيشٗاۖ وَلِبَاسُ ٱلتَّقۡوَىٰ ذَٰلِكَ خَيۡرٞۚ
ذَٰلِكَ مِنۡ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ لَعَلَّهُمۡ يَذَّكَّرُونَ ﴿٢٦﴾ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ لَا يَفۡتِنَنَّكُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ كَمَآ أَخۡرَجَ
أَبَوَيۡكُم مِّنَ ٱلۡجَنَّةِ يَنزِعُ عَنۡهُمَا لِبَاسَهُمَا لِيُرِيَهُمَا سَوۡءَٰتِهِمَآۚ إِنَّهُۥ يَرَىٰكُمۡ هُوَ وَقَبِيلُهُۥ
مِنۡ حَيۡثُ لَا تَرَوۡنَهُمۡۗ إِنَّا جَعَلۡنَا ٱلشَّيَٰطِينَ أَوۡلِيَآءَ لِلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ ﴿٢٧﴾

**26-27.** የአደም ልጆች ሆይ፣ ሀፍረተ ገላችሁን የሚሸሽግን ልብስና ጌጥን በእርግጥ በእናንተ ላይ አወረድን። አላህን የመፍራት ልብስ የተሻለ ነው። ይህ ከአላህ ተዐምራቶች ነው። ይገሰፁ ዘንድ አወረደላቸው። የአደም ልጆች ሆይ! ሰይጣን አባትና እናታችሁን ሀፍረተ ገላቸውን ሊያሳያቸው ልብሶቻቸውን ከእነርሱ የገፈፋቸው ሲሆን ከገነት እንዳወጣቸው ሁሉ እናንተንም አይሞክራችሁ። እነሆ እርሱ ከእነሰራዊቱ ከማታዩዋቸው ስፍራ ያያቿሀልና። እኛ ሰይጣናትን ለእነዚያ ለማያምኑት ወዳጆች አድርገናል።

وَإِذَا فَعَلُواْ فَٰحِشَةٗ قَالُواْ وَجَدۡنَا عَلَيۡهَآ ءَابَآءَنَا وَٱللَّهُ أَمَرَنَا بِهَاۗ قُلۡ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَأۡمُرُ
بِٱلۡفَحۡشَآءِۖ أَتَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٢٨﴾ قُلۡ أَمَرَ رَبِّي بِٱلۡقِسۡطِۖ وَأَقِيمُواْ وُجُوهَكُمۡ
عِندَ كُلِّ مَسۡجِدٖ وَٱدۡعُوهُ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَۚ كَمَا بَدَأَكُمۡ تَعُودُونَ ﴿٢٩﴾

**28-29.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መጥፎንም ሥራ በሠሩ ጊዜ፦ በእርሷ ላይ አባቶቻችንን አገኘን። አላህም በእርሷ አዞናል ይላሉ፦ አላህ በመጥፎ ነገር አያዝም በአላህ ላይ የማታውቁትን ትናገራላችሁን? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ በማስተካከል በፍትህ አዘዘ። በየመስገጃ ቦታ ዘንድም ፊቶቻችሁን እርሱን ለመገዛት አስተካክሉ። ሃይማኖትንም ለእርሱ ብቻ ፍፁም አድርጋችሁ አምልኩ። መጀመሪያ እርሱ እንደፈጠራችሁ በመጨረሻም ወደ እርሱ ትመለሳላችሁና በላቸው።

فَرِيقًا هَدَىٰ وَفَرِيقًا حَقَّ عَلَيۡهِمُ ٱلضَّلَٰلَةُۚ إِنَّهُمُ ٱتَّخَذُواْ ٱلشَّيَٰطِينَ أَوۡلِيَآءَ مِن دُونِ ٱللَّهِ
وَيَحۡسَبُونَ أَنَّهُم مُّهۡتَدُونَ ﴿٣٠﴾

**30.** ከፊሉን ወደ ቅን መንገድ መራ። ከፊሎቹም ደግሞ በእነርሱ ላይ ጥመት ተረጋግጦባቸዋል። እነርሱ ሰይጣናትን ከአላህ ሌላ ረዳቶች አድርገው ይዘዋልና። እነርሱም ቅኑን መንገድ የተመራን ነን ብለው ያስባሉ።

۞ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ خُذُواْ زِينَتَكُمۡ عِندَ كُلِّ مَسۡجِدٖ وَكُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ وَلَا تُسۡرِفُوٓاْۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ
ٱلۡمُسۡرِفِينَ ٣١ قُلۡ مَنۡ حَرَّمَ زِينَةَ ٱللَّهِ ٱلَّتِيٓ أَخۡرَجَ لِعِبَادِهِۦ وَٱلطَّيِّبَٰتِ مِنَ ٱلرِّزۡقِۚ قُلۡ هِيَ
لِلَّذِينَ ءَامَنُواْ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا خَالِصَةٗ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۗ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٣٢

**31-32.** የአደም ልጆች ሆይ! ሀፍረተ ገላችሁን የሚሸፍኑትን ጌጦቻችሁን በየመስገጃው ሁሉ ዘንድ ያዙ። ብሉ ጠጡም ግን አታባክኑ። (እርሱ) አባካኞችን አይወድምና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያችን ለባሮች የፈጠራትን የአላህን ጌጥ ከሲሳይ ጥሩዎቹን እርም ያደረገ ማን ነው? በላቸው። እርሷ በትንሳኤ ቀን ለነዚያ በትክክል ላመኑት ሰዎች ብቻ ስትሆን በቅርቢቱ ህይወትም ተገቢያቸው ናት በላቸው። ልክ እንደዚሁ ለሚያውቁ ህዝቦች አንቀፆችን እናብራራለን።

قُلۡ إِنَّمَا حَرَّمَ رَبِّيَ ٱلۡفَوَٰحِشَ مَا ظَهَرَ مِنۡهَا وَمَا بَطَنَ وَٱلۡإِثۡمَ وَٱلۡبَغۡيَ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّ وَأَن
تُشۡرِكُواْ بِٱللَّهِ مَا لَمۡ يُنَزِّلۡ بِهِۦ سُلۡطَٰنٗا وَأَن تَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٣٣ وَلِكُلِّ أُمَّةٍ
أَجَلٞۖ فَإِذَا جَآءَ أَجَلُهُمۡ لَا يَسۡتَأۡخِرُونَ سَاعَةٗ وَلَا يَسۡتَقۡدِمُونَ ٣٤

**33-34.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ እርም ያደረገው የተገለፀም ሆነ የተደበቀን መጥፎ ስራን ኃጢአትን፣ ያለ አግባብ መበደልንም በእርሱም ማስረጃ ያላወረደበትን ጣኦት በአላህ ማጋራታችሁንና በአላህ ላይ የማታውቁትን መናገራችሁን ብቻ ነው በላቸው። ለህዝቦች ሁሉ የተወሰነ ጊዜ አላቸው። እናም ጊዜያቸው በደረሰ ወቅት አንዷትን ሰዓት (በማንም ሐይል) አይቆዩም። ከጊዜያቱም አይቀድሙምም።

يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ إِمَّا يَأۡتِيَنَّكُمۡ رُسُلٞ مِّنكُمۡ يَقُصُّونَ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِي فَمَنِ ٱتَّقَىٰ وَأَصۡلَحَ
فَلَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ٣٥ وَٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَٱسۡتَكۡبَرُواْ عَنۡهَآ أُوْلَٰٓئِكَ
أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٣٦

**35-36.** የአደም ልጆች ሆይ! ከናንተ መካከል አንቀፆቼን የሚያነቡላችሁ መልዕክተኞች ቢመጡላችሁ ከናንተ ክህደትን የተጠነቀቁና በጎንም ተግባር የሠሩ ሰዎች ሁሉ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው አያዝኑምም። እነዚያ በአንቀፆቻችን ያስተባበሉና ከእርሷ የኮሩ ሰዎች ሁሉ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱም በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው።

فَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِـَٔايَـٰتِهِۦٓ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ يَنَالُهُمْ نَصِيبُهُم مِّنَ
ٱلْكِتَـٰبِ ۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَتْهُمْ رُسُلُنَا يَتَوَفَّوْنَهُمْ قَالُوٓا۟ أَيْنَ مَا كُنتُمْ تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ ۖ
قَالُوا۟ ضَلُّوا۟ عَنَّا وَشَهِدُوا۟ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ أَنَّهُمْ كَانُوا۟ كَـٰفِرِينَ ٣٧

37. በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጠፈ ወይም በየ አናቅፅ ካስዋሸ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው? እነዚያ ከተጻፈላቸው ከመጽሐፉ ውስጥ ሲሆን ድርሻቸው ያገኛቸዋል። የሞት መልዕክተኞቻችን የሚገድሏቸው ሆነው በመጡባቸው ጊዜ ከአላህ ሌላ ትገዟቸው የነበራችሁት የት አሉ ይሏቸዋል። ከእኛ ተሰወሩን ይላሉ። እነርሱም ከሓዲያን እንደነበሩ በነፍሶቻቸው ላይ ይመሰክራሉ።

قَالَ ٱدْخُلُوا۟ فِىٓ أُمَمٍ قَدْ خَلَتْ مِن قَبْلِكُم مِّنَ ٱلْجِنِّ وَٱلْإِنسِ فِى ٱلنَّارِ ۖ كُلَّمَا دَخَلَتْ أُمَّةٌ
لَّعَنَتْ أُخْتَهَا ۖ حَتَّىٰٓ إِذَا ٱدَّارَكُوا۟ فِيهَا جَمِيعًا قَالَتْ أُخْرَىٰهُمْ لِأُولَىٰهُمْ رَبَّنَا هَـٰٓؤُلَآءِ أَضَلُّونَا
فَـَٔاتِهِمْ عَذَابًا ضِعْفًا مِّنَ ٱلنَّارِ ۖ قَالَ لِكُلٍّ ضِعْفٌ وَلَـٰكِن لَّا تَعْلَمُونَ ٣٨ وَقَالَتْ أُولَىٰهُمْ
لِأُخْرَىٰهُمْ فَمَا كَانَ لَكُمْ عَلَيْنَا مِن فَضْلٍ فَذُوقُوا۟ ٱلْعَذَابَ بِمَا كُنتُمْ تَكْسِبُونَ ٣٩

38-39. ከአጋንንትና ከሰው ከናንተ በፊት በእርግጥ ካለፉት ህዝቦች ጋር ሆናችሁ እሳት ውስጥ ግቡ ይላቸዋል። አንዲቱ ቡድን ህዝብ ወደ እሳት በገባች ቁጥር ያሳሳተቻትን ብጤዋን ቡድን ትረግማለች። መላውም በውስጧ ተሰብስበው በተገናኙ ጊዜ የኋለኛይቱ ቡድን ለመጀመሪያይቱ ቡድን (ተከታዮች ለአስከታዮች)፡- ጌታችን ሆይ! እነዚህ አሳሳቱን ከእሳትም ስቃይ እጥፍን ስጣቸው ትላለች። አላህም፡- ለሁሉም እጥፍ አለው ግን አታውቁም ይላቸዋል። መጀመሪያይቱም ቡድን ለኋለኛይቱ ቡድን ለእናንተ በእኛ ላይ ምንም ብልጫ አልነበራችሁም ትላለች። ትሠሩትም በነበራችሁት ቅጣቱን ቅመሱ ይላቸዋል።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَـٰتِنَا وَٱسْتَكْبَرُوا۟ عَنْهَا لَا تُفَتَّحُ لَهُمْ أَبْوَٰبُ ٱلسَّمَآءِ وَلَا يَدْخُلُونَ
ٱلْجَنَّةَ حَتَّىٰ يَلِجَ ٱلْجَمَلُ فِى سَمِّ ٱلْخِيَاطِ ۚ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلْمُجْرِمِينَ ٤٠ لَهُم مِّن جَهَنَّمَ
مِهَادٌ وَمِن فَوْقِهِمْ غَوَاشٍ ۚ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلظَّـٰلِمِينَ ٤١

**40-41.** እነዚያ አንቀፆቻችንን ያስተባበሉና ከእርሷም የኮሩ ሰዎች ሁሉ ለእነርሱ የሰማይ ደጃፎች አይከፈቱላቸውም። ግመል በመርፌ ቀዳዳ እስከሚገባ ድረስ ገነትን አይገቡም። ልክ እንደዚሁ አጋሪዎችን እንቀጣለን። ለእነርሱም (በሥራቸው ምክንያት) ከገሀነም እሳት ምንጣፍ ከበላያቸውም የእሳት መሸፈኛዎች አሉባቸው። ልክ እንደዚሁ በደለኞችን እንቀጣለን።

وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَا نُكَلِّفُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَآ أُو۟لَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلْجَنَّةِ ۖ
هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٤٢﴾ وَنَزَعْنَا مَا فِى صُدُورِهِم مِّنْ غِلٍّ تَجْرِى مِن تَحْتِهِمُ ٱلْأَنْهَٰرُ ۖ وَقَالُوا۟
ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ٱلَّذِى هَدَىٰنَا لِهَٰذَا وَمَا كُنَّا لِنَهْتَدِىَ لَوْلَآ أَنْ هَدَىٰنَا ٱللَّهُ ۖ لَقَدْ جَآءَتْ رُسُلُ رَبِّنَا
بِٱلْحَقِّ ۖ وَنُودُوٓا۟ أَن تِلْكُمُ ٱلْجَنَّةُ أُورِثْتُمُوهَا بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿٤٣﴾

**42-43.** እነዚያም በአላህ ያመኑና መልካሞችን የሰሩ ማንኛውንም ነፍስ የችሎታዋን እንጂ አናስገድድምና እነዚያ የገነት ሰዎች ናቸው። እነርሱም በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ሁሉ ጥላቻም እናስወግዳለን። ወንዞች በሥሮቻቸው ይፈሳሉ። ለዚያም ወደዚህ ለአደረሰን ሥራ ለመራን ለአላህ ብቻ ምስጋና ይገባው። አላህ ባልመራን ኖሮ ወደዚህ አንመራም ነበር። የጌታችን መልዕክተኞች በእውነት ላይ ሲሆኑ መጥተውልናል ይላሉ። ይህ ገነት ትሠሩት በነበራችሁት እንድትወርሱት የተደረጋችሁት ነው በማለት ይጠራሉ።

وَنَادَىٰٓ أَصْحَٰبُ ٱلْجَنَّةِ أَصْحَٰبَ ٱلنَّارِ أَن قَدْ وَجَدْنَا مَا وَعَدَنَا رَبُّنَا حَقًّا فَهَلْ وَجَدتُّم مَّا
وَعَدَ رَبُّكُمْ حَقًّا ۖ قَالُوا۟ نَعَمْ ۚ فَأَذَّنَ مُؤَذِّنٌۢ بَيْنَهُمْ أَن لَّعْنَةُ ٱللَّهِ عَلَى ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٤٤﴾ ٱلَّذِينَ
يَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَيَبْغُونَهَا عِوَجًا وَهُم بِٱلْءَاخِرَةِ كَٰفِرُونَ ﴿٤٥﴾

**44-45.** የገነት ሰዎች የእሳት ሰዎችን ጌታችን ቃል የገባልንን እውነት ሆኖ አገኘን እናንተስ ጌታችሁ የዛተባችሁን እውነት ሆኖ አገኛችሁትን? ሲሉ ይጣራሉ። (የእሳት ሰዎችም) አዎን አገኘን ይላሉ። በመካከላቸውም የአላህ እርግማን በበደለኞች ላይ ይሁን ሲል አዋጅ ነጋሪ ያውጃል። በደለኞች ማለት እነዚያ ከአላህ መንገድ ሌሎችን ክፍሎች የሚከለክሉና የአላህ መንገድ እንድትጣመም የሚፈልጉ እነርሱም በመጨረሻዋ ዓለም ከሓዲያን የሆኑ ሰዎች ብቻ ናቸው።

وَبَيْنَهُمَا حِجَابٌۚ وَعَلَى ٱلْأَعْرَافِ رِجَالٌ يَعْرِفُونَ كُلًّۢا بِسِيمَىٰهُمْۚ وَنَادَوْاْ أَصْحَٰبَ ٱلْجَنَّةِ أَن
سَلَٰمٌ عَلَيْكُمْۚ لَمْ يَدْخُلُوهَا وَهُمْ يَطْمَعُونَ ﴿٤٦﴾ ۞وَإِذَا صُرِفَتْ أَبْصَٰرُهُمْ تِلْقَآءَ أَصْحَٰبِ
ٱلنَّارِ قَالُواْ رَبَّنَا لَا تَجْعَلْنَا مَعَ ٱلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٤٧﴾

**46-47.** በጀነት ሰዎችና በገሀነም ሰዎች መካከል አዕራፍ የሚባል ከባድ መጋረጃ አለ። በአዕራፍ ላይ ሁሉንም በምልክታቸው የሚያውቁ ሰዎች አሉ። የገነትን ሰዎች ሰላም ለእናንተ ይሁን በማለት ይጣራሉ። እነርሱም (የአዕራፍ ሰዎች) ጀነት መግባትን የሚከጅሉ ሲሆኑ ገና እንዲገቡ አልተደረጉም። ዓይኖቻቸው ወደ እሳት ሰዎች አቅጣጫ በተዞሩ ጊዜ:- ጌታችን ሆይ! እባክህ ከበደለኞች ሰዎች ጋር አታድርገን ይላሉ።

وَنَادَىٰٓ أَصْحَٰبُ ٱلْأَعْرَافِ رِجَالًا يَعْرِفُونَهُم بِسِيمَىٰهُمْ قَالُواْ مَآ أَغْنَىٰ عَنكُمْ
جَمْعُكُمْ وَمَا كُنتُمْ تَسْتَكْبِرُونَ ﴿٤٨﴾ أَهَٰٓؤُلَآءِ ٱلَّذِينَ أَقْسَمْتُمْ لَا يَنَالُهُمُ ٱللَّهُ بِرَحْمَةٍۚ
ٱدْخُلُواْ ٱلْجَنَّةَ لَا خَوْفٌ عَلَيْكُمْ وَلَآ أَنتُمْ تَحْزَنُونَ ﴿٤٩﴾

**48-49.** የአዕራፍም* ሰዎች በምልክታቸው የሚያውቋቸውን (ታላላቅ) ሰዎች ይጠራሉ። ብዛታችሁና ኩራታችሁ ከናንተ ምንም አልጠቀማችሁ ይሏቸዋል። እነዚያ የአላህ ችሮታው አይደርሳቸውም ብላችሁ የማላችሁት ወገኖች ናቸውን? ገነትን ግቡ።(አሁን ግን) ፍርሃት የለባችሁም። እናንተም አታዝኑም (ተባሉ ይሏቸዋል)።

✶ የአዕራፍ ሰዎች ማለት መልካም ስራቸው ከመጥፎ ስራቸው ጋር እኩል ለእኩል የሆነባቸው ናቸው።

وَنَادَىٰٓ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ أَصْحَٰبَ ٱلْجَنَّةِ أَنْ أَفِيضُواْ عَلَيْنَا مِنَ ٱلْمَآءِ أَوْ مِمَّا رَزَقَكُمُ ٱللَّهُۚ
قَالُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ حَرَّمَهُمَا عَلَى ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٥٠﴾ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ دِينَهُمْ لَهْوًا وَلَعِبًا وَغَرَّتْهُمُ ٱلْحَيَوٰةُ
ٱلدُّنْيَاۚ فَٱلْيَوْمَ نَنسَىٰهُمْ كَمَا نَسُواْ لِقَآءَ يَوْمِهِمْ هَٰذَا وَمَا كَانُواْ بِـَٔايَٰتِنَا يَجْحَدُونَ ﴿٥١﴾

**50-51.** የእሳት ሰዎች የገነትን ሰዎች በእኛ ላይ ውሃ ወይም አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይ እባካችሁ አፍስሱልን ብለው ይጠሯቸዋል። የገነት ሰዎችም እነዚህ ሲሳዮች እኮ አላህ በከሓዲያን ላይ እርም አድርጓቸዋል ይሏቸዋል። እነዚያ ሃይማኖታቸውን መሳለቂያና መጫወቻ አድርገው የያዙና የቅርቢቱ ህይወት ያታለለቻቸው የዚህን ቀን መገናኘታቸውን እንደ ረሱና በተአምራቶቻችን ይክዱ እንደ ነበሩ ሁሉ ዛሬ እኛም እንረሳቸዋለን (እንተዋቸዋለን)።

ከሱረቱ አል አዕራፍ (31) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ በጃሂሊያ ጊዜ (ቅደመ ኢስላም የመሀይምነት ወቅት) ሴቶች ካዕባን ሲጠውፉ እራቁታቸውን ይጠውፉ ነበርና ይህ ድርጊታቸው ሕገ ወጥ መሆኑን ለማጋለጥ አላህ እነዚህን አናቅፅ አወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻህ እንዳስተላለፉት «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) የፈጅር ሶላት ሲያሰግዱ፤ የተወሰኑ እንስት ምእመናን ፊቶቻቸውን በመሸፋፈን ከእሳቸው ጋር ፈጅርን ሶላት ለመገኘት ወደ መስጂድ ይመጡ ነበር። ከዚያ በኋላ ሶላቱ ከተጠናቀቀ በኋላ ማንም ሳያውቃቸው ወደየቤቶቻቸው ይመለሱ ነበር» ብለዋል።

**ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (23-51) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፦**

1. የሰው ዘር መነሻ አባታችን አደምና እናታችን ሐዋ ጥፋታቸውን አምነው ይቅርታን ከአላህ ለመለመን ፀሎት አድርገው የነበረው በዚህ ቃል መሆኑን፤
2. ከንስሃ ቅድመ ሁኔታዎች ጥፋትን አምኖ ይቅርታ መጠየቅ አንዱ መሆኑን፤
3. ኢብሊስ ያባረረውና ለአባታችን አደም ከጀነት መውጣት ዋነኛው ምክንያት ወንጀልን መዳፈራቸው መሆኑን፤
4. የሰው ልጅ ኑሮውም ሆነ ከሞት በኋላም መቀበሪያው (መመለሻው) ይህችው መሬት መሆኗን፤
5. የአላህ ጸጋና ውለታ በእጅጉ ማስታወስና ማመስገን ተገቢ መሆኑን፤
6. ከሰይጣን ተንኮልና የማሳሳት እርምጃ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ መሆኑን፤
7. ሰይጣን ሰዎችን ሊያይ የሚችል ሰዎች ግን እርሱን ለማየት የማይችሉ መሆኑን፤
8. በአላህ ፈጣሪነትና አምላክነት በምላስ ወይም በተግባር የካዱ ከሓዲያን የሰይጣን ወዳጆች መሆናቸው፤
9. ብልሹ ስነምግባሮችና መጥፎ ባህሪያት የተወገዙ ከመሆናቸውም ባሻገር ጸያፍ መሆናቸውን፤
10. የአላህ ህግጋትና ድንጋጌዎች እንጂ የማንም ሰው ተግባር ሃይማኖታዊ ማስረጃ ሆኖ ሊቀርብ እንደማይችል፤
11. አላህ መጥፎ ነገሮችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ሰዎችን ሊያዛቸው ቀርቶ ስሜታቸውን ተከትለው በሚሰሩት መጥፎ ስራ ቅር እንደሚለው እና እንደሚያዝን፤
12. አላህ የፈቀደውን መከልከል ትልቅ ወንጀል ስለመሆኑ፤
13. ለትክክለኛ አማኞች ምድራዊ መጠቀሚያ የተፈቀደላቸው ከመሆኑም በላይ እነዚህን የአላህ ፀጋዎች የመጠቀም ቅድሚያ የሚሰጠው ከከሃዲያኖች ይልቅ ለሙስሊሞች መሆኑን፤
14. ዝሙት፤ ግብረ ሰዶም እና የመሳሰሉት ብልሹ ምግባራት ለማህበራዊ ቀውስ፤ ለምድራዊ ነውጥና ምስቅልቅል ህይወት ምክንያት መሆናቸው፤
15. የእያንዳንዱ ሰው የእድሜ ጣሪያ ገደብና የህይወቱ መጥፊያ ምክንያት አስቀድሞ በአላህ የተወሰነ መሆኑን፤
16. ሰዎች ላለማመናቸው የሚያቀርቧቸው ውድቅ ምክንያቶች በሙሉ አላህ ነብያትን በመላክ ተቀባይነት ሊኖረው በማይችል ሁኔታ ለምክንያቶቻቸው በር መዝጋቱ፤
17. የአላህ ፍራቻ በልብ ውስጥ መስረፁን ከሚያረጋግጡ ተግባራት ዋነኛው ሺርክን መጠንቀቅ መሆኑን፤
18. ማስተባበል (የአላህን መንገድ ያለመከተል) እና ኩራት የአላህ ፍራቻ በሌለበት ልብ ውስጥ የሚቀመጡ የመልካምነት ተቃራኒ ተግባራት መሆናቸውን፤
19. በአላህ ላይ ውሸትን መቅጠፍ ከግፎች ሁሉ የከፋ ግፍ ስለመሆኑ፤

20. በቀብር ውስጥ ፈተና አዘል ጥያቄዎች መኖራቸውንና ለወንጀለኞችና ለከሓዲያን የቀብር ቅጣትም እንደማይቀርላቸው፤
21. በወንጀላቸውና በክህደታቸው የገሀነም (ጀሀነም) ቅጣት የተወሰነባቸው የጀሀነም ሰዎች እርስ በእርሳቸው እንደሚወቃቀሱ፤
22. አስተባባዮችና ኩራተኞች የጀነትን ተድላ የሚነፈጉ ከመሆኑም በላይ ቅጣት እንደሚፈረድባቸው እንረዳለን።
23. መልካም ሥራ ለጀነት የሚያበቃና መጨረሻው ለባለቤቱ የሚጠቅም ስለመሆኑ፤
24. ነብያት ያስተማሯቸው ተስተምህሮዎች ትክክለኛ እምነትን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ መሆናቸውንና እነዚያ እምነታዊ ትእዛዛትና ድንጋጌዎች ከሰዎች አቅም በላይ ያለመሆናቸውን፤
25. በጀነት (ገነት) ውስጥ ጠብም ሆነ ምቀኝነት የሌሉ መሆናቸውን፤
26. ቅኑን መንገድ መመራት (ሂዳያ) የአላህ ስጦታ እንጂ በጉልበትና እውቀት ወይም ከሌላ ሰው የሚገኝ ባለመሆኑ ሂዳያን (መመራትን) ከአላህ እንጂ ከሌላ መጠየቅ የተከለከለ መሆኑን፤
27. ነብያት በአላህ ፍቃድ የተናገሯቸው ትንቢታዊ ንግግሮች ተግባራዊ ሆነው እንደሚታዩ ቁርኣናዊ ማረጋገጫዎች እንዳለ፤
28. የጀሃነም ሰዎችና የጀነት ሰዎች ሲፈልጉ እርስ በርሳቸው የሚያወሩባቸው (የሚነጋገሩባቸው) እና የሚተያዩባቸው አጋጣሚዎች እንደሚኖሩ፤
29. ሰዎች የአላህን ዲን እንዲያውቁና ተግባራዊ እንዳያደርጉ እንቅፋት መሆን ከፍተኛ ወንጀል ስለመሆኑ፤
30. የትንሳኤ እለት ምድራዊ ስራዎቹ ሚዛን ላይ ሲቀመጡ የመልካም ሥራዎች ክብደት ከመጥፎ ስራዎቹ በልጦ ሚዛኑ የደፋለት ሰው ከገሀነም ቅጣት ነፃ እንደሚወጣ፤ በአንፃሩም የመልካም ሥራው ከመጥፎ ሥራው ጋር እኩል ሚዛን የመጣበት ሰው ከተወሰኑ ሂደቶች (ከአዕራፍ ቆይታ በኋላ) ወደ ጀነት እንደሚገባ፤
31. አንድን ነገር በሙሉ ልብ ባገኘው ብሎ መመኘት የሚቻለው ጉዳዩን ለማግኘት የሚያበቁ ቅድመ ሁኔታዎችን ከተወጡ በኋላ መሆን እንዳለበት፤
32. በማጋራት ውስጥ ተዘፍቀው የሞቱ ሰዎችን የገንዘብ ሃይልም ሆነ የዘመድ ብዛት ከአላህ ቅጣት እንደማይታደጋቸው።
33. በምድራዊ ህይወት ቆይታቸው በሰዎች ይናቁ የነበሩ ትክክለኛ አማኞች በጀነት የተበሰሩ ስለመሆኑ፤
34. በሃይማኖት ጉዳይ ላይ መቀለድና ማፌዝ እንዲሁም በድንጋጌዎቹ ማላገጥ የተከለከለ መሆኑን፤
35. ሰው ምንም ያህል ባለሀብትና ባለፀጋ ቢሆንም አኼራን ረስቶ በዱንያ መታለልና ለዱንያ ብቻ መሮጥ የተፈጠረለትን አላማ መርሳት በመሆኑ መዘናጋት እንደማይገባ እንማራለን።

وَلَقَدْ جِئْنَٰهُم بِكِتَٰبٍ فَصَّلْنَٰهُ عَلَىٰ عِلْمٍ هُدًى وَرَحْمَةً لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿٥٢﴾ هَلْ يَنظُرُونَ
إِلَّا تَأْوِيلَهُۥ ۚ يَوْمَ يَأْتِى تَأْوِيلُهُۥ يَقُولُ ٱلَّذِينَ نَسُوهُ مِن قَبْلُ قَدْ جَآءَتْ رُسُلُ رَبِّنَا بِٱلْحَقِّ
فَهَل لَّنَا مِن شُفَعَآءَ فَيَشْفَعُوا۟ لَنَآ أَوْ نُرَدُّ فَنَعْمَلَ غَيْرَ ٱلَّذِى كُنَّا نَعْمَلُ ۚ قَدْ خَسِرُوٓا۟
أَنفُسَهُمْ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَفْتَرُونَ ﴿٥٣﴾

**52-53.** ከእውቀት ጋር የዘረዘርነው መጽሐፍ ለሚያምኑ ህዝቦች መመሪያና እዝነት ሲሆን አወረድንላቸው። የዛቻውን ፍጻሜ እንጂ ሌላ አይጠባበቁም። ፍጻሜው በሚመጣበት ቀን ግን እነዚያ ከመምጣቱ በፊት የረሱት ሰዎች የጌታችን መልዕክተኞች በእውነት መጥተዋል። እና ለእኛ ያማልዱን ዘንድ አማላጆች አሉን? ወይስ ከዚያ እንሠራው ከነበርነው የተለየ ስራ እንድንሰራ ዕድሉ ይሰጠናል? ይላሉ። በእርግጥም ራሳቸውን ይከስራሉ። ይቀጥፉት የነበረው ሁሉ ከንቱ ሆኖ ያገኙታል።

إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰ عَلَى ٱلْعَرْشِ يُغْشِى ٱلَّيْلَ ٱلنَّهَارَ يَطْلُبُهُۥ حَثِيثًا وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ وَٱلنُّجُومَ مُسَخَّرَٰتٍۭ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ أَلَا لَهُ ٱلْخَلْقُ وَٱلْأَمْرُ ۗ تَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٥٤﴾

**54.** (ሰዎች ሆይ) ጌታችሁ አላህ ያ! ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ፈጠረና ከዚያም በዐርሹ ላይ ከፍ አለ።* ቀኑንም በሌሊቱ ይሸፍነዋል። ሁለቱም እርስ በእርስ በፍጥነት ይፈላለጋሉ። ፀሐይ ጨረቃና ከዋክብት በትዕዛዙ የተገሩ ናቸው። (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተውሉ! መፍጠርም ማዘዝም የእርሱ ነው። የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ ክብሩ ላቀ።

* አላህ በዐርሹ ላይ ከፍ ስለማለቱ ከዚህ አንቀፅ ሌላም በተመሳሳይ በስድስት አናቅፅ ላይም በግልፅ የተወሳ ሲሆን በትክክለኛ ሀዲሶችም እንደዚሁ መግለጫ ተስጥቶበታል። በዚሁ ቃል ባይሆንም በተመሳሳይ ቃል የአላህን የበላይነት የሚገልፁ አያሌ የቁርአንና የሐዲስ መረጃዎች አሉ። ስለዚህ ጉዳይ በዋናው ተፍሲር ላይ ጠቃሚ ማብራሪያ ከተቢያለሁና (ጽፌያለሁና) ተጠቀሙበት። የሱናና የህብረት ባለቤቶች (አህለ ሱና ወል ጀማዓ) በዚህ ርዕስ ስለ አላህ ባህሪ (ሲፋት) ጥበቃ ቁርአንና ሐዲስን መሰረት ያደረገ ንግግርን በመናገር ይረዳሉ። በቁርአንና በሐዲስ በተዘገቡት በአላህ ስሞችና ባህሪያት ሁሉ ያምናሉ። አላህ ራሱን በገለጸበት ከፍጡሩ ሁሉ ስለ እሱ ይበልጥ የሚያቁትና ያለምንም ማራቆትና መቀየር ነብዩ (ﷺ) እና እንደዚሁም ሰለፎች አላህን በገለፁበት መንገድ ይገልፁታል።

አህለ ሱና ወል ጀማዓ ስለ አላህ ባህሪና ስሞች ቁርአንና ሃዲስ የተናገረውን ነቢዩ (ሰ ዐ ወ) እና ሰሐቦች የነቢዩ (ﷺ) (ባልደረቦች) እንደዚሁም ሰለፎች በተረዱበት አረዳድ ያለ ምንም ማራቆትና ያለ ምንም በፍጡራን ማመሳሰል ይረዱታል

ከዚህ ጋ በአላህ ባህሪ ዙሪያ ሁለት ነገሮች በጥብቅ የተከለከሉ ናቸው:-

1.እንዴት ሁኖ ነው ያለው (ከይፍ) የሚል ጥያቄ ማምጣት በፍጹም የተከለከለ ነው

2.ፈጣሪን በማንኛውም ፍጡር ማመሳሰል በጭራሽ የተከለከለ ነው።

በዚህ ዙሪያ ብዙ ቁርአንና ሐዲስ ተነግረዋል ከእነዚህ መካከል:- ይኸው አሁን የያዝነው አንቀፅ:-

1.ኛ. «ጌታችሁ አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ ነው። ከዚያም በዐርሹ ላይ ከፍ አለ።» (አል. አዕራፍ: 54)

2.ኛ. «ጌታችሁ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ አላህ ነው ከዚያም ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብር ሲሆን በአርሹ ላይ ከፍ አለ ከእርሱ ፈቃድ በኋላ ቢሆን እንጂ አንድም አማላጅ የለም ይሃችሁ አላህ ጌታችሁ ነውና ተገዙት። አትገሰጹምን?» (ዩኑስ፡ 3)

3.ኛ. «አላህ ያ ሰማያትን የምታዩዋት አዕማድ ሳትኖር ያነሳት ከዚያም በአርሹ ላይ ከፍ አለ ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ነው። ሁሉም የተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ ነገሩን ሁሉ ያስተናብራል በጌታችሁ መገናኘት ያረጋግጡ ዘንድ ተዓምራቶችን ይዘረዝራል» (አል-ረዕድ፡ 2)

4.ኛ. «(እርሱ) አል. ረህማን ነው በአርሹ ላይ ከፍ አለ» (ጡሃ፡ 5)

5.ኛ. «ያ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ከዚያም በአርሹ ላይ ከፍ አለ አልረህማን ነው ከርሱም አዋቂን ጠይቅ» (አል-ፉርቃን፡ 59)

6.ኛ. «አላህ ያ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ከዚያም በአርሹ ላይ ከፍ ያለ ነው ከእርሱ ሌላ ለእናንተ ረዳትም አማላጅም ምንም የላችሁም አትገሰጹምን?» (አልሰጅዳህ፡ 4)

7.ኛ. «እርሱ ያ ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ የፈጠረ ከዚያም በዙፋኑ ላይ ከፍ አለ። በምድር ውስጥ የሚገባውን ከእርሷም የሚወጣውን ከሰማይም የሚወርደውን በእርሷም ውስጥ የሚያርገውን ያውቃል። እርሱም የትም ብትሆኑ ከእናንተ ጋር ነው አላህም የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነው» (አልሀዲድ፡ 41)

8.ኛ. አላህ ሌሊትን በቀን ፈጥኖ የሚፈልገው ሲሆን ይሸፍናል። ፀሐይን ጨረቃንና ከዋክብትን በትዕዛዙ የተገሩ ሲሆኑ ፈጠራቸው ንቁ መፍጠርና ማዘዝ የእርሱ ስልጣን ብቻ ነው። የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ ክብሩ ላቀ።

9.ኛ. ይህን ጉዳይ በተመለከተ ነብዩ እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ የመላክት ቡድን ማታ ከአንተ ጋር ይቆያል ሁለቱ ቡድኖች በአስርና በፈጅር ሰላቶች ይገናኛሉ። ከዚያም በማታ ካንተ ጋር የቆዩት (ወደ ሰማይ) ይወጣሉ አላህም እያወቀ ስለ አንተ ይጠይቃቸዋል...» (ቡኻሪ፤ ሙስሊምና ነሳኢ የዘገቡት ሐዲስ)

10.ኛ. «አላህ ፍጥረታትን ፈጥሮ ሲያበቃ «የእኔ ራህመት (ርህራሄ) ከኔ ቁጣ ይቀድማል» በማለት ከዙፋኑ በላይ በሆነ ከእርሱ ጋር ባለው መፅሐፍ ውስጥ ጻፈ» አቡዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ «ለአብዛሃኞች አላህ ያዝናል። ምድር ላሉት እዘኑ። ከሰማይ በላይ ያለው አላህ እንዲያዝንላችሁ»

11.ኛ. በኡሁድ ተራራ አል. ጀዋሪያ በምትባል ቦታ አቅራቢ በጎቼን የምትጠብቅልኝ አንዲት ሴት አገልጋይ (ባሪያ) ነበረችኝ። አንድ ቀን በጎቼን ለማየት ስሄድ ተኩላ አንዷን በግ ወስዷታል። እንደማንኛውም የአደም ልጅ (የሰው ልጅ) እኔም ስህተት መሥራቴ ስለማይቀር ፊቷን በጥፊ ክፉኛ መታኋት። ከዚያም ወደ ነብዩ መጥቼ ሁኔታውን ስነግራቸው በጣም ከባድ ወንጀል መስራቴን አሳሰቡኝ። "የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! (ከባርነት) ነጻ ላደርጋት አልችልምን? አልኳቸው "እስቲ ወደ እኔ አምጣት" አሉኝ። ከዚያም አመጣኋት። "አላህ የት ነው ያለው? ሲሉ ጠየቋት "ከሰማይ በላይ" ስትል መለሰች። እኔስ ማን ነኝ" በማለት ጠየቋት። "አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ነዎት። በማለት መለሰችላቸው። ከዚያም "በእርግጥ እሷ እውነተኛ አማኝ ስለሆነች ነጻ አድርጋት። " (ገፅ 123 አል. በዛር በአል. ከሀፍ ገፅ 37 የዘገቡት ሐዲስ)

12.ኛ. «አላህ አለ ግን የትም ቦታ የለም (አቅጣጫም ሆነ ቦታ የለውም)» እንደሚሉት እውነታ ቢሆን ኖሮ "ከሰማይ በላይ ነው ብላ ለነቢዩ (ﷺ) መልስ የሰጠችውን ሴት መልስ ባስተካከሏት ነበር። እርሳቸው ግን መቀበል ብቻ ሳይሆን በእርሷ ምላሽ እውነተኛ አማኝ መሆኗንም መስከሩላት።

**13.ኛ.** አቡዘር ባወሩትና ኢማሙ ሙስሊም በዘገቡት ሰሂህ ሐዲስ ደግሞ አቡዘር ነብዩ (ﷺ) በሚዕራጅ ጉዟቸው ሰማያትን አልፈው ወደ አላህ ሲሄዱ ጌታቸውን አላህን አይተው እንደሆነ “ጌታዎትን አይተዋልን” በማለት ጠየቋቸው። ነብዩም (ﷺ) አላህን እንዳላዩ “ብርሃንን ነው ያየሁት” በማለት መለሱ። በመሰረቱ ሶሀቦች ነብዩ ጌታቸው ዘንድ መሄዳቸውን ባያውቁ ኖሮ “ጌታዎትን አይተዋል ወይ» በማለት ባልጠየቋቸው ነበር። አላህ ከሰማይ በላይ ባለው አቅጣጫ አለ ብሎ በማመን “ጌታዎትን አይተዋልን” በማለት ነብዩም (ﷺ) ሲጠየቁ ጥያቄው ስህተት ቢሆን ኖሮ “አላህ እኮ ቦታም ሆነ አቅጣጫ የለውም” በማለት ሶሃቦችን አያርሙም ነበርን?

**14.ኛ.** (ቡኻሪ፤ አል. ዳሪሚ፤ ረድ አለል ሚሪሲ ገፅ **463**) አቡበከር አስሲዲቅ ነብዩ (ﷺ) ሲሞቱ እንዲህ ብለዋል፦ «ሙሐመድን የሚገዛ ካለ ሙሐመድ በእርግጥ ሞቷል። አላህ ግን ህያው ሲሆን ከሰማይ በላይ ነው አይሞትምም።»

**15.ኛ.** ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ከሰዎች ጋር በመሆን በመንገድ ላይ እየሄዱ ሳለ “አንዲት አሮጊት አስቆመቻቸውና ይነጋገሩ ጀመር። ከዑመር ጋር ከነበሩት አንዱ ማን እንደሆነች አውቀሃልን? ይህች ሴት አላህ ከሰባት ሰማያት በላይ ሆኖ ስሞታዋን የሰማላት ኸውላ ቢንት ሰዕለባ ነች እኮ። «አላህ የዚያችን በባሏ ነገር የምትከራከርህንና ወደ አላህ የምትሰሙተውን (ሴት ቃል በእርግጥ ሰማ» (አልሙጃደላህ፡ **1**) በርሷ ምክንያት ነው ይህ የቁርአን አንቀፅ የወረደው። ወላሂ! በሌሊት ወደኔ መጥታ ብታስቆመኝ ትቻት አልሄድም ለሰላት ካልሆነ በቀር ሰላቴንም ቢሆን ሰግጄ እመለሳለሁ። ዳሪሚ ረድ እለልል ጀህሚያ ገፅ **26**፤ ኢብኑ ሀጀር በአል ኢስባህና (**7\62**)፤ ኢብኑ ከሲር (**8\61**)።

**16.ኛ.** ኢማሙ አሻፊዒ፦ ኢማሙ አብዱራህማን፤ ኢብኑ አቡሃቲም አል ራዚ፤ ከአቡሹዐይብና አቡሰውር ሙሀመድ ኢብኑ ኢድሪስ አልሻፊዒ እንዲሁ ማለታቸውን ዘግበውታል፡ የሀዲሱ ባለቤቶችን ስላገኘሁበትና እንደ ሱፍያን ኢማሙ ማሊክና ከሌሎቹ እንደ ወሰዱኩት እና እኔ ስላለሁበት ሱና “ከአላህ ሌላ ፈጣሪ አለመኖሩን እመሰክራለሁ። ሃያሉ አላህ ከዓርሹ በላይ ስለመሆኑ እመሰክራለሁ። ዓርሹም ከሰማይ በላይ ነው። ወደ ፈለገው ፍጡር በፈለገው መልኩ ይቀርባል። ሀያሉ አላህ ወደ ምድር ሰማይ በፈለገው ሁኔታ ይወርዳል።

ታዋቂው ዓሊም አብዱልቃድር ጀይላኒ አላህ ከዓርሽ በላይ ስለመሆኑ እንዲህ በማለት ይገልጻሉ፡ “እርሱ አላህ ከዓርሹ በላይ ነው። ነብዩ (ﷺ) ያችን ሴት አገልጋይ “አላህ የትነው ያለው? በማለት በጠየቋት ጊዜ ወደ ላይ ጠቁማ በማሳየቷ አማኝ መሆንዋን መስክረውላታል። የአራህማን ዓርሽ ከውሃ በላይ ነው። አላህ ከዓርሽ በላይነው ያለው” (አል ጉንያህ በተባለው መጾሐፉቸው ገፅ **54**፤ **56**፤ **57**)

ٱدْعُوا۟ رَبَّكُمْ تَضَرُّعًا وَخُفْيَةً ۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ ٱلْمُعْتَدِينَ ﴿٥٥﴾ وَلَا تُفْسِدُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ بَعْدَ إِصْلَٰحِهَا وَٱدْعُوهُ خَوْفًا وَطَمَعًا ۚ إِنَّ رَحْمَتَ ٱللَّهِ قَرِيبٌ مِّنَ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٥٦﴾

**55-56.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ጌታችሁን ተናንሳችሁና ተዋርዳችሁ በድብቅ ለምኑት። እርሱ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና። በምድር ውስጥ ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። አላህን ፈርታችሁና ከጅላችሁ ተገዙት። የአላህ ችሮታ ለበጎ አድራጊዎች ሁሉ ቅርብ ነውና።*

✶ በአዕራፍም 59፤ 65 ና 85 ላይ እንደተገለፀው ሁሉም ነብያት ለህዝቦቻቸው ...ማለታቸው ተዘግቧል። ነብያትም 25 ኛው አንቀፅ እንዲህ ይላል። ከዚህ በመነሳት የማንም አባት ዘመድ ወገን አይደለም። «ሌሊትና ቀንም ፀሀይና ጨረቃም ከምልክቶች ናቸው ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ ለዚያም ለፈጠራችሁ አላህ ስገዱ። እነርሱን ብቻ የምትገዙ እንደሆናችሁ ለሌላ አትስገዱ» (ፉሲለት፡ 37) «አላህ ስልጣኑን ለማንም አይሰጥም። በግድም ማንም አይወስድበትም» (አል. ከህፍ፡ 26) እና (ሰበእ፡ 22) ይህን እውነት ያስረዳሉ። የስልጣንን እንኳንስ ሊተባበር ሊሰጥ አይደለም አለኝ ብሎ በወሬ ደረጃ እንኳን ተናገረ ውዮለት። ቁርኣን... ነብያትም 29 ይላል። ሰዎች ጌታቸውን በዚህ መልኩ ከተረዱትና ከልባቸው የተሳሰቡ ግንዛቤዎች ከተወገዱ የነቢያት የተላኩት ቀጥተኛው መስመር ብቻ ይቀራል። 2 ኛ. ሰዎችን ትክክለኛውን መንገድ ማስረዳትና ትክክኛው ነገር ማስተማር ነው። ይህም ተግባር ትዕግስትና ፅናት ያስፈልገዋል። በመሬት ሙሉ ሽርክ የሌለበት ወንጀል ይዞ የመጣ ሰው እሷን ሚሞላ ምህረት እሰጠዋለሁ።

ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «አላህ ረህመትን ለመቶ ከፍሏል። ከዚያም ዘጠና ዘጠኝ እርሱ አስቀርቶ አንዱን ክፍል ብቻ ወደ ምድር አወረደ። በዚሁ ክፍል ነው ፍጡሮች እርስ በርሳቸው የሚተዛዘኑት ...ለልጇ ስታጠባ ስትረግጠው እግሯን የምታነሳውም በዚሁ ክፍል ነው» ብለዋል። አላህ መቶ ረህመት አሉት። ከዚሁ መካከል ለሰዎችና ለጋኔል፤ ለእንስሳት ለዕፅዋት አንዷትን ብቻ አወረደ። እናም በሱ ይተዛዘናሉ። አውሬዎች ለልጆቻቸው ያዝኑባታል። እሱ ዘንድ ዘጠና ዘጠኝ አስቀርቶ በትንሳኤ እለት ለባሮቹ ያዝንበታል።

የአላህ እዝነት ሲል ምን ያህል መጠነ ሰፊ እንደሆነ ነብዩ ሲናገሩ «አላህ ሰማይና ምድርን በፈጠረበት ጊዜ መቶ ራህመቶችን ፈጠረ። እያንዳንዱ ራህመት በሰማይና በምድር መካከል ያለውን የሚሞላ ነው» ብለዋል። እነዚህና መሰል ሐዲሶች በትክክለኛ ዘገባ ተዘግበዋል። የነብዩ (ﷺ) ሐዲሶች በቁርኣን ከተወሱት የአላህን ሩህሩህነት የሚያመለክቱ ትምህርቶች ጋር ሲደመሩ በሰው ልጅ ከሺርክ እነሱን እስካ...ድረስ በአላህ ራህመት እንደማይበልጥ እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ሊሰመርበት የሚገባው ወሳኝ ነጥብ ቢኖር አላህን ስንገዛው ጀነትን ፈልገንና እሳትን ፈርተን መሆን ያለበት መሆኑን ነው።

وَهُوَ ٱلَّذِى يُرۡسِلُ ٱلرِّيَٰحَ بُشۡرَۢا بَيۡنَ يَدَىۡ رَحۡمَتِهِۦۖ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَقَلَّتۡ سَحَابًا ثِقَالًا سُقۡنَٰهُ لِبَلَدٖ مَّيِّتٖ فَأَنزَلۡنَا بِهِ ٱلۡمَآءَ فَأَخۡرَجۡنَا بِهِۦ مِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِۚ كَذَٰلِكَ نُخۡرِجُ ٱلۡمَوۡتَىٰ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ٥٧ وَٱلۡبَلَدُ ٱلطَّيِّبُ يَخۡرُجُ نَبَاتُهُۥ بِإِذۡنِ رَبِّهِۦۖ وَٱلَّذِى خَبُثَ لَا يَخۡرُجُ إِلَّا نَكِدٗاۚ كَذَٰلِكَ نُصَرِّفُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَشۡكُرُونَ ٥٨

**57-58.** እርሱ (አላህ) ያ! ነፍሶችን ከዝናብም በፊት አብሳሪዎች አድርጎ የሚልክ ነው። ከባዶችንም ደመናዎች በተሸከሙ ጊዜ ሙት ወደ ሆነ አገር እንነዳዋለን። በእነርሱም ውሃን እናወርዳለን። እናም ከፍሬዎች ሁሉ በእነርሱ እናወጣለን። ልክ እንደዚሁ ሙታንን ከመቃብር እናስወጣለን። (ይህን የምንለው) ትገነዘቡ ዘንድ ነው። መልካሙ አገር በጌታው ፈቃድ በቃዩ ያማረ ሆኖ ይወጣል። ያ፣ መጥፎ የሆነው ደግሞ በቃዩ ደካማ ሆኖ እንጂ አይወጣም። ልክ እንደዚሁ ለሚያመሰግኑ ህዝቦች ታምራትን እናብራራለን።

لَقَدْ أَرْسَلْنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوْمِهِۦ فَقَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥٓ إِنِّىٓ أَخَافُ
عَلَيْكُمْ عَذَابَ يَوْمٍ عَظِيمٍ ﴿٥٩﴾ قَالَ ٱلْمَلَأُ مِن قَوْمِهِۦٓ إِنَّا لَنَرَىٰكَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٦٠﴾
قَالَ يَٰقَوْمِ لَيْسَ بِى ضَلَٰلَةٌ وَلَٰكِنِّى رَسُولٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦١﴾ أُبَلِّغُكُمْ رِسَٰلَٰتِ رَبِّى
وَأَنصَحُ لَكُمْ وَأَعْلَمُ مِنَ ٱللَّهِ مَا لَا تَعْلَمُونَ ﴿٦٢﴾ أَوَعَجِبْتُمْ أَن جَآءَكُمْ ذِكْرٌ مِّن رَّبِّكُمْ
عَلَىٰ رَجُلٍ مِّنكُمْ لِيُنذِرَكُمْ وَلِتَتَّقُوا۟ وَلَعَلَّكُمْ تُرْحَمُونَ ﴿٦٣﴾ فَكَذَّبُوهُ فَأَنجَيْنَٰهُ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥ
فِى ٱلْفُلْكِ وَأَغْرَقْنَا ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَآ ۚ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ قَوْمًا عَمِينَ ﴿٦٤﴾

**59-64.** ነብዩ ኑሕን ወደ ወገኖቹ ላክነው። ከዚያ:- ወገኖቼ ሆይ፣ አላህን ተገዙ። ለእናንተ ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። እኔ በእናንተ ላይ የከባድ ቀንን ቅጣት እፈራላችኋለሁ አላቸው። ከህዝቦቹ መካከል በአላህ የካዱት መሪዎቹ እኛ በግልጽ ስህተት ውስጥ ሆነህ እናይሀለን አሉት። ኑህም ወገኖቼ ሆይ ምንም መሳሳት የለብኝም። ግን እኔ ከዓለማት ጌታ መልዕክተኛ ነኝ አላቸው። የጌታዬን መልዕክቶች አደርስላችኋለሁ። ለናንተም እመክራችኋለሁ። ከአላህ በኩል የማታውቁትን አውቃለሁ። ኑህም አላህን ልትፈሩና ይታዘንላችሁም ዘንድ ከናንተው ጎሳ መካከል በሆነ ሰው ላይ እንዲያስጠነቅቃችሁ ከጌታችሁ ግሳጼ ስለመጣላችሁ ትደነቃላችሁን? (አላቸው)። ወዲያውም አስተባበሉት። እርሱንና እነዚያንም ከእርሱ ጋር ያሉትን አማኞች በታንኳዋ ውስጥ አዳንናቸው። እነዚያን በአንቀፆቻችን ያስተባበሉትን ሰዎች ግን በባህር አሰመጥናቸው። እነርሱ ልበ እውራን ህዝቦች ነበሩና።

۞ وَإِلَىٰ عَادٍ أَخَاهُمْ هُودًا ۗ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥٓ ۚ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴿٦٥﴾
قَالَ ٱلْمَلَأُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِن قَوْمِهِۦٓ إِنَّا لَنَرَىٰكَ فِى سَفَاهَةٍ وَإِنَّا لَنَظُنُّكَ مِنَ ٱلْكَٰذِبِينَ ﴿٦٦﴾
قَالَ يَٰقَوْمِ لَيْسَ بِى سَفَاهَةٌ وَلَٰكِنِّى رَسُولٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٧﴾ أُبَلِّغُكُمْ رِسَٰلَٰتِ رَبِّى
وَأَنَا۠ لَكُمْ نَاصِحٌ أَمِينٌ ﴿٦٨﴾ أَوَعَجِبْتُمْ أَن جَآءَكُمْ ذِكْرٌ مِّن رَّبِّكُمْ عَلَىٰ رَجُلٍ مِّنكُمْ
لِيُنذِرَكُمْ ۚ وَٱذْكُرُوٓا۟ إِذْ جَعَلَكُمْ خُلَفَآءَ مِنۢ بَعْدِ قَوْمِ نُوحٍ وَزَادَكُمْ فِى ٱلْخَلْقِ بَصْۜطَةً ۖ
فَٱذْكُرُوٓا۟ ءَالَآءَ ٱللَّهِ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٦٩﴾ قَالُوٓا۟ أَجِئْتَنَا لِنَعْبُدَ ٱللَّهَ وَحْدَهُۥ وَنَذَرَ مَا كَانَ
يَعْبُدُ ءَابَآؤُنَا ۖ فَأْتِنَا بِمَا تَعِدُنَآ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴿٧٠﴾ قَالَ قَدْ وَقَعَ عَلَيْكُم مِّن

رَّبِّكُمْ رِجْسٌ وَغَضَبٌ ۖ أَتُجَٰدِلُونَنِى فِىٓ أَسْمَآءٍ سَمَّيْتُمُوهَآ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُم مَّا نَزَّلَ ٱللَّهُ بِهَا
مِن سُلْطَٰنٍ ۚ فَٱنتَظِرُوٓا۟ إِنِّى مَعَكُم مِّنَ ٱلْمُنتَظِرِينَ ﴿٧١﴾ فَأَنجَيْنَٰهُ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥ بِرَحْمَةٍ مِّنَّا
وَقَطَعْنَا دَابِرَ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا ۖ وَمَا كَانُوا۟ مُؤْمِنِينَ ﴿٧٢﴾

**65-72.** ወደ ዐድም ወንድማቸውን ነብዩ ሁድን ላክን፡ ወገኖቼ ሆይ! አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። የአላህን ቅጣት አትፈሩምን? አላቸው። ከህዝቦቹ መካከል እነዚያ በአላህ የካዱት መሪዎች። እኛ በሞኝነት ላይ ሆነህ እናይሀለን። እኛም ከውሸተኞቹ ነህ ብለንም እንጠረጥርሀለን አሉት። እርሱም፡- ወገኖቼ ሆይ! እኔ ሞኝነት የለብኝም። ግን እኔ ከአለማት ጌታ የተላኩ ነኝ አላቸው። የጌታዬን መልዕክቶች አደርስላችኋለሁ። እኔም ለእናንተ ታማኝና መካሪ ነኝና። ከጌታችሁ የሆነ ግሳጼ ከናንተው ውስጥ በሆነ በአንድ ሰው ላይ ያስጠነቅቃችሁ ዘንድ ስለመጣባችሁ ትደነቃላችሁን? ከነብዩ ኑህ ህዝቦች በኋላ ምትኮች ባደረጋችሁና በፍጥረትም ግዙፍነትን በጨመረላችሁ ጊዜ የሆነውን አስታውሱ። የሻችሁትን ታገኙ ዘንድ የአላህን ፀጋዎች አስታውሱ። አላህን አንድ አድርገን ብቻውን እንድንገዛውና አባቶቻችን ይገዟቸው የነበሩትን አማልክት እንድንተው መጣህብን?። እውነተኛ ከሆንክ የምታስፈራራበትን ቅጣት እስቲ አምጣብን አሉ። ሰዎች ከጌታችሁ የሆነ ቅጣትና ቁጣ በእናንተ ላይ በእውነት ተረጋገጠ። እናንተና አባቶቻችሁ (አማልዕክት ብላችሁ) በጠራችኋቸው ስሞች አላህ በእነርሱ ምንም ማስረጃ ባላወረደባቸው ትከራከሩኛላችሁን? ተጠባበቁ እኔም ከናንተ ጋር ከተጠባባቂዎቹ ነኝና አለ። እርሱንና እነዚያን አብረውት የነበሩትን አማኞችን በችሮታችን (ከቅጣት) አዳንናቸው። የእነዚያንም በተአምራታችን ያስተባበሉትንና አማኞች ያልነበሩትን ሰዎች ሙሉ ለሙሉ አጠፋን።

وَإِلَىٰ ثَمُودَ أَخَاهُمْ صَٰلِحًا ۗ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥ ۖ قَدْ جَآءَتْكُم
بَيِّنَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ ۖ هَٰذِهِۦ نَاقَةُ ٱللَّهِ لَكُمْ ءَايَةً ۖ فَذَرُوهَا تَأْكُلْ فِىٓ أَرْضِ ٱللَّهِ ۖ وَلَا تَمَسُّوهَا
بِسُوٓءٍ فَيَأْخُذَكُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٧٣﴾ وَٱذْكُرُوٓا۟ إِذْ جَعَلَكُمْ خُلَفَآءَ مِنۢ بَعْدِ عَادٍ وَبَوَّأَكُمْ
فِى ٱلْأَرْضِ تَتَّخِذُونَ مِن سُهُولِهَا قُصُورًا وَتَنْحِتُونَ ٱلْجِبَالَ بُيُوتًا ۖ فَٱذْكُرُوٓا۟ ءَالَآءَ ٱللَّهِ
وَلَا تَعْثَوْا۟ فِى ٱلْأَرْضِ مُفْسِدِينَ ﴿٧٤﴾ قَالَ ٱلْمَلَأُ ٱلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُوا۟ مِن قَوْمِهِۦ لِلَّذِينَ
ٱسْتُضْعِفُوا۟ لِمَنْ ءَامَنَ مِنْهُمْ أَتَعْلَمُونَ أَنَّ صَٰلِحًا مُّرْسَلٌ مِّن رَّبِّهِۦ ۚ قَالُوٓا۟ إِنَّا بِمَآ أُرْسِلَ

بِهِۦ مُؤۡمِنُونَ ﴿٧٥﴾ قَالَ ٱلَّذِينَ ٱسۡتَكۡبَرُوٓاْ إِنَّا بِٱلَّذِيٓ ءَامَنتُم بِهِۦ كَٰفِرُونَ ﴿٧٦﴾ فَعَقَرُواْ
ٱلنَّاقَةَ وَعَتَوۡاْ عَنۡ أَمۡرِ رَبِّهِمۡ وَقَالُواْ يَٰصَٰلِحُ ٱئۡتِنَا بِمَا تَعِدُنَآ إِن كُنتَ مِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿٧٧﴾
فَأَخَذَتۡهُمُ ٱلرَّجۡفَةُ فَأَصۡبَحُواْ فِي دَارِهِمۡ جَٰثِمِينَ ﴿٧٨﴾ فَتَوَلَّىٰ عَنۡهُمۡ وَقَالَ يَٰقَوۡمِ لَقَدۡ
أَبۡلَغۡتُكُمۡ رِسَالَةَ رَبِّي وَنَصَحۡتُ لَكُمۡ وَلَٰكِن لَّا تُحِبُّونَ ٱلنَّٰصِحِينَ ﴿٧٩﴾

**73-79.** ወደ ሰሙድም ህዝቦች ወንድማቸውን ነብዩ ሷሊህን ላክን። ወገኖቼ ሆይ! አላህን ብቻ ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ ምንም አምላክ የላችሁም። እውነተኛ ለመሆኔ ከጌታችሁ የሆነች ምልክት በእርግጥ መጥታላችኋለች። ይህች ለእናንተ ተዐምር ስትሆን የአላህ ግመል ናትና ተዋት። በአላህ ምድር ውስጥ እንደፈለገች ትብላ፤ (ትጠጣም)። በክፉ አትንኳትም። አሳማሚ ቅጣት ይይዛችኋልና። ከዓድ ህዝቦችም በኋላ ምትኮች ባደረጋችሁና በምድሪቱም ላይ ባስቀመጣችሁ ጊዜ የሆነውን አስታውሱ። ከሜዳ ሸክላ ሕንጻዎችን ትገነባላችሁ። ከተራራዎችም ቤቶችን ትጠርባላችሁ። ስለዚህ የአላህን ፀጋዎች አስታውሱ። በምድርም ውስጥ አጥፊዎች ሆናችሁ አታበላሹ። ከወገኖቹ መካከል እነዚያ የኮሩት መሪዎች ለእነዚያ ለተሸነፉት በተለይም ከእነርሱ ላመኑት፡ ክፍሎች ሷሊህ ከጌታው መላኩን ታውቃላችሁን? አሏቸው። እነርሱም አዎን እናውቃለን። እኛ እርሱ በተላከበት ነገር ሁሉ አማኞች ነን አሉ። እነዚያ የኮሩት እኛ ግን በዚያ ባመናችሁበት ነገር ከሓዲዎች ነን አሉ። እናም ወዲያው ግመሊቱን ወጓትና ከጌታቸው ትዕዛዝ ወጡ። ሷሊህ ሆይ! ከመልዕክተኞቹ እንደሆንክ የምታስፈራራብንን (ቅጣት) አምጣብን አሉ። ወዲያውም የምድር መንቀጥቀጥ (ጩኸት) ያዘቻቸው። በየቤቶቻቸውም ውስጥ ተደፍተው አደሩ። ሷሊህ ከነርሱ ዞረና ወገኖቼ ሆይ፣ የጌታዬን መልዕክት በእርግጥ አደረስኩላችሁ። ለእናንተም መከርኳችሁ። ግን እናንተ መካሪዎችን አትወዱም አለ።

وَلُوطًا إِذۡ قَالَ لِقَوۡمِهِۦٓ أَتَأۡتُونَ ٱلۡفَٰحِشَةَ مَا سَبَقَكُم بِهَا مِنۡ أَحَدٖ مِّنَ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٨٠﴾ إِنَّكُمۡ
لَتَأۡتُونَ ٱلرِّجَالَ شَهۡوَةٗ مِّن دُونِ ٱلنِّسَآءِۚ بَلۡ أَنتُمۡ قَوۡمٞ مُّسۡرِفُونَ ﴿٨١﴾ وَمَا كَانَ جَوَابَ قَوۡمِهِۦٓ إِلَّآ
أَن قَالُوٓاْ أَخۡرِجُوهُم مِّن قَرۡيَتِكُمۡۖ إِنَّهُمۡ أُنَاسٞ يَتَطَهَّرُونَ ﴿٨٢﴾ فَأَنجَيۡنَٰهُ وَأَهۡلَهُۥٓ إِلَّا ٱمۡرَأَتَهُۥ
كَانَتۡ مِنَ ٱلۡغَٰبِرِينَ ﴿٨٣﴾ وَأَمۡطَرۡنَا عَلَيۡهِم مَّطَرٗاۖ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ﴿٨٤﴾

**80-84.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ነብዩ ሉጥን ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ) ከዓለማት ከናንተ በፊት አንድም ህዝብ ያልፈፀመውን አስቀያሚ ሥራ ትሠራላችሁን? እናንተ ከሴቶች ሌላ ወንዶችን በመከጀል ትመጡባቸዋላችሁ። እናንተ ወሰንን አላፊ ሕዝቦች ናችሁ። የሕዝቦቹም መልስ ሉጥንና ተከታዮቹን ከከተማችሁ አውጧቸው። እነርሱ የሚጥራሩ ሰዎች ናቸውና። ከማለት ሌላ አልነበረም። ከዚያ እርሱንና ቤተሰቦቹን አዳንናቸው ሚስቱ ብቻ ስትቀር። እርሷማ ለጥፋት ከቀሩት ሰዎች ሆነች። በእነርሱ ላይ (የእሳት) ዝናብን አዘነብንባቸው (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የኃጢአተኞች መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ ተመልከት።

وَإِلَىٰ مَدۡيَنَ أَخَاهُمۡ شُعَيۡبٗاۚ قَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥۖ قَدۡ جَآءَتۡكُم
بَيِّنَةٞ مِّن رَّبِّكُمۡۖ فَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ وَٱلۡمِيزَانَ وَلَا تَبۡخَسُواْ ٱلنَّاسَ أَشۡيَآءَهُمۡ وَلَا تُفۡسِدُواْ فِي
ٱلۡأَرۡضِ بَعۡدَ إِصۡلَٰحِهَاۚ ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ٨٥ وَلَا تَقۡعُدُواْ بِكُلِّ صِرَٰطٖ
تُوعِدُونَ وَتَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ مَنۡ ءَامَنَ بِهِۦ وَتَبۡغُونَهَا عِوَجٗاۚ وَٱذۡكُرُوٓاْ إِذۡ كُنتُمۡ قَلِيلٗا
فَكَثَّرَكُمۡۖ وَٱنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٨٦ وَإِن كَانَ طَآئِفَةٞ مِّنكُمۡ ءَامَنُواْ بِٱلَّذِيٓ
أُرۡسِلۡتُ بِهِۦ وَطَآئِفَةٞ لَّمۡ يُؤۡمِنُواْ فَٱصۡبِرُواْ حَتَّىٰ يَحۡكُمَ ٱللَّهُ بَيۡنَنَاۚ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلۡحَٰكِمِينَ ٨٧

**85-87.** ወደ መድየን ሕዝብም ወንድማቸውን ነብዩ ሹዓይብን ላክን። አላቸውም። ወገኖቼ ሆይ! አላህን ብቻ ተገዙ። ከእርሱ በቀር ምንም አምላክ የላችሁም። ከጌታችሁ ዘንድ ግልጽ ማስረጃ መጥቶላችኋል። ስፍርንና ሚዛንን ሙሉ። የሰዎችንም ገንዘቦቻቸውን አታጉድሉባቸው። ምድርንም ከተበጀች በኋላ አታበላሹ። ትክክለኛ አማኞች ከሆናችሁ ይህ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው። ሰዎችን የምታስፈራሩ፤ ከአላህም መንገድ በእርሱ ያመኑትን የምታግዱና የአላህን መንገድ መጥመሟንም የምትፈልጓት ሆናችሁ በየመንገዱ አትቀመጡ። ጥቂቶች በነበራችሁና ባበዛችሁ*1 ጊዜ የሆነውን አስታውሱ። የአጥፊ ህዝቦች መጨረሻ እንዴት እንደነበረም ተመልከቱ። ከናንተም መካከል እኔ በተላኩበት ያመኑ ቡድኖችና ያላመኑ ቡድኖች ቢኖሩ በመካከላችን አላህ እስከሚፈርድ ታገሡ። እርሱ ከፈራጆች ሁሉ እጅግ በላጭ ነው።*2

*1 ብዛት በኢስላም እንደ ጥራት ሁሉ ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠው ባይሆንም የራሱ የሆነ ጥቅም እንዳለው ግን አይካድም።

*2 (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አዋጅ እያንዳንዳችሁ ጠባቂዎች ናችሁ። ስለምትጠብቁት ነገርም ተጠያቂዎች ናችሁ። በሰዎች ዘንድ መሪ የሆነ ሰው ጠባቂ ነው። ስለሚጠብቀው ነገርም ተጠያቂ ነው። አንድ ሰው

በቤተሰቡ ላይ ጠባቂ ነው። ስለሚጠብቀው ነገርም ተጠያቂ ነው። አንዲት ሴት በባሏ ቤትና በልጆቹ ላይ ጠባቂ ነች። ስለምትጠብቀው ነገርም ተጠያቂ ነች። አንድ አገልጋይ ባሪያ በአስተዳዳሪው ንብረት ላይ ጠባቂ ነው። ስለሚጠብቀው ነገርም ተጠያቂ ነው። አዋጅ! እያንዳንዳችሁ ተጠባቂዎች ናችሁ» ስለምትጠብቁት ነገርም ተጠያቂዎች ናችሁ»

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ጡረይፍ አቡ ተይሚያህ እንዳስተላለፉት፡- «ጁንዱብ፤ ሰፋዋንና ጓዶኞቹን ሲመክራቸው ተመልክቻለሁ፤ እንዲሁም ሲሉ ጠየቁት «ከአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) አንዳች ነገር ሰምተኻልን?» እሱም «አዎን እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ። «አንድን ነገር ሰዎች እንዲሰሙለት ብሎ የተናገረ አላህ በትንሳኤ ቀን ደብቋቸው የነበሩትን ሚስጢሮች ለሰዎች ያሰማበታል» ሰዎችን ለከባድ ችግር የሚያጋልጥ ሰው፤ አላህ በትንሳኤ ቀን ከባድ ችግር ላይ ይጥለዋል። ጓደኞቹም «ምከረን» አሉት። እሱም «ከሰው ልጅ አካል ውስጥ በቅድሚያ የሚጠነባው ሆዱ ነው። ከመልካም ነገር በስተቀር ሌላን የማይመገብ ሰው ይህን ያድርግ። በእሱና በጀነት መካከል በእጁ በፈሰሰው ደም ሳቢያ መራራቅ እንዳይኖር ለማድረግ የቻለ ሰው ይህን ይፈፅም» «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ከመልካም ነገር በስተቀር የማይመገብ ሰው ይህን ያድርግ» ማለታቸው (መልካም ነገሮችን ለመብላት ፈቃኛ ያልሆነ በትንሳኤ ቀን ሆዱ እንደሚጠነባ ያመለክታል። ከዚህ መከራ ለመጠበቅ የሰው ልጅ «እስካልተገደደ ድረስ በሀላል ነገሮች ብቻ መመገብ ይኖርበታል» የሚለውን ያሳያል።

(ሐ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት «እኔና ነብዩ (ﷺ) ከመስጂድ እየወጣን ሳለን አንድ ሰው መስጂድ በር ላይ አገኘንና «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የትንሳኤ ቀን መቼ ነው?» ሲል ጠየቀ፡- እሳቸውም «ለእሷ ምንስ አዘጋጅተህላታል?» ሲሉ ጠየቁት። ሰውየውም አፈር በማለት ፈራ ተባ እያለ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከፆምና ከሶላት ዘካህ ከመስጠት የበለጠ ለመስራት አልተዘጋጀሁም። ዳሩ ግን አላህንና መልዕክተኛውን እወዳለሁ» አለ። እሳቸውም «አንተ ከምትወደው ጋር ትሆናለህ» አሉት።

(መ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ዘር እንዳስተላለፉት፡- «በአንድ ወቅት ወደ ነብዩ ስሄድ እንዲህ አሉ፤ «ነፍሴ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ! ግመሎች ወይም ላሞች ወይም በጎች እያሉት ከነርሱ ዘካህ የማይሰጥ ማንኛውም ሰው በትንሳኤ ቀን እንስሶቹ በጣም ትልቅና የሰቡ ሆነው ወደርሱ በመምጣት ከኮቴዎቻቸው ስር ይረግጡታል። በቀንዶቻቸውም ይወጉታል። በየተራ ይፈራረቁበታል። የመጨረሻው ተራውን ሲጨርስ የመጀመሪያው እንደገና ጀምራል። ይህም ቅጣት አላህ በሰዎች ላይ ያለውን ፍርድ እስኪያጠናቅቅ ድረስ በሰውየው ላይ ይቀጥላል»

۞قَالَ ٱلْمَلَأُ ٱلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُواْ مِن قَوْمِهِۦ لَنُخْرِجَنَّكَ يَٰشُعَيْبُ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَعَكَ مِن
قَرْيَتِنَآ أَوْ لَتَعُودُنَّ فِى مِلَّتِنَا ۚ قَالَ أَوَلَوْ كُنَّا كَٰرِهِينَ ﴿٨٨﴾ قَدِ ٱفْتَرَيْنَا عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا إِنْ
عُدْنَا فِى مِلَّتِكُم بَعْدَ إِذْ نَجَّىٰنَا ٱللَّهُ مِنْهَا ۚ وَمَا يَكُونُ لَنَآ أَن نَّعُودَ فِيهَآ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ
رَبُّنَا ۚ وَسِعَ رَبُّنَا كُلَّ شَىْءٍ عِلْمًا ۚ عَلَى ٱللَّهِ تَوَكَّلْنَا ۚ رَبَّنَا ٱفْتَحْ بَيْنَنَا وَبَيْنَ قَوْمِنَا بِٱلْحَقِّ وَأَنتَ
خَيْرُ ٱلْفَٰتِحِينَ ﴿٨٩﴾ وَقَالَ ٱلْمَلَأُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن قَوْمِهِۦ لَئِنِ ٱتَّبَعْتُمْ شُعَيْبًا إِنَّكُمْ إِذًا
لَّخَٰسِرُونَ ﴿٩٠﴾ فَأَخَذَتْهُمُ ٱلرَّجْفَةُ فَأَصْبَحُواْ فِى دَارِهِمْ جَٰثِمِينَ ﴿٩١﴾ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ شُعَيْبًا
كَأَن لَّمْ يَغْنَوْاْ فِيهَا ۚ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ شُعَيْبًا كَانُواْ هُمُ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٩٢﴾ فَتَوَلَّىٰ عَنْهُمْ وَقَالَ يَٰقَوْمِ
لَقَدْ أَبْلَغْتُكُمْ رِسَٰلَٰتِ رَبِّى وَنَصَحْتُ لَكُمْ ۖ فَكَيْفَ ءَاسَىٰ عَلَىٰ قَوْمٍ كَٰفِرِينَ ﴿٩٣﴾

**88-93.** *ከህዝቦቹ መካከል እነዚያ የኮሩት መሪዎች፦ ሹአይብ ሆይ! አንተንና እነዚያን ከአንተ ጋር ያመኑትን ከከተማችን እናስወጣችኋለን ወይም ወደ ሃይማኖታችን መመለስ አለባችሁ አሉ። እርሱም የጠላንም ብንሆን? አላቸው። አላህ ከእርሷ ከአዳነን በኋላ ወደ ሃይማኖታችሁ ብንመለስ በአላህ ላይ ውሸትን ቀጠፍን። አላህ ጌታችን ካልሻም በስተቀር ወደ እርሷ ልንመለስ አይገባንም። የጌታችን እውቀቱ ከሁሉ ሰፋ። በአላህ ላይ ብቻ ተመካን ጌታችን ሆይ! በእኛና በወገኖቻችን መካከል ፍረድ። አንተም ከፈራጆቹ ሁሉ በላጭ ነህና (አለ)። ከወገኖቹም መካከል እነዚያ በአላህ የካዱት መሪዎች ለሕዝቡ ሹአይብን ብትከተሉ ከሳሪዎች ናችሁ አሉ። ወዲያውኑ የምድር መንቀጥቀጥ ጩኸትም ያዘቻቸው። በየቤታቸው ውስጥ ተደፍተው አደሩ። እነዚያ ነብዩ ሹዓይብን ያስተባበሉት ሰዎች በቤቶቻቸው እንዳልነበሩባት ሆኑ። እነዚያ ነብዩ ሹዓይብን ያስተባበሉት ከሳሪዎች እነርሱ ብቻ ሆኑ። ሹአይብም ትቷቸው ከእነርሱ ዞረና ወገኖቼ ሆይ! የጌታዬን መልእክቶች በእርግጥ አደረስኩላችሁ ለእናንተም መከርኩ። ታዲያ በከሃዲ ሰዎች ላይ እንዴት አዝናለሁ? አለ።

* ክፍል ዘጠኝ

وَمَآ أَرۡسَلۡنَا فِي قَرۡيَةٖ مِّن نَّبِيٍّ إِلَّآ أَخَذۡنَآ أَهۡلَهَا بِٱلۡبَأۡسَآءِ وَٱلضَّرَّآءِ لَعَلَّهُمۡ يَضَّرَّعُونَ ٩٤
ثُمَّ بَدَّلۡنَا مَكَانَ ٱلسَّيِّئَةِ ٱلۡحَسَنَةَ حَتَّىٰ عَفَواْ وَّقَالُواْ قَدۡ مَسَّ ءَابَآءَنَا ٱلضَّرَّآءُ وَٱلسَّرَّآءُ
فَأَخَذۡنَٰهُم بَغۡتَةٗ وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ٩٥ وَلَوۡ أَنَّ أَهۡلَ ٱلۡقُرَىٰٓ ءَامَنُواْ وَٱتَّقَوۡاْ لَفَتَحۡنَا عَلَيۡهِم
بَرَكَٰتٖ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَٰكِن كَذَّبُواْ فَأَخَذۡنَٰهُم بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٩٦ أَفَأَمِنَ
أَهۡلُ ٱلۡقُرَىٰٓ أَن يَأۡتِيَهُم بَأۡسُنَا بَيَٰتٗا وَهُمۡ نَآئِمُونَ ٩٧ أَوَأَمِنَ أَهۡلُ ٱلۡقُرَىٰٓ أَن يَأۡتِيَهُم بَأۡسُنَا
ضُحٗى وَهُمۡ يَلۡعَبُونَ ٩٨ أَفَأَمِنُواْ مَكۡرَ ٱللَّهِۚ فَلَا يَأۡمَنُ مَكۡرَ ٱللَّهِ إِلَّا ٱلۡقَوۡمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٩٩
أَوَلَمۡ يَهۡدِ لِلَّذِينَ يَرِثُونَ ٱلۡأَرۡضَ مِنۢ بَعۡدِ أَهۡلِهَآ أَن لَّوۡ نَشَآءُ أَصَبۡنَٰهُم بِذُنُوبِهِمۡۚ وَنَطۡبَعُ
عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ فَهُمۡ لَا يَسۡمَعُونَ ١٠٠ تِلۡكَ ٱلۡقُرَىٰ نَقُصُّ عَلَيۡكَ مِنۡ أَنۢبَآئِهَاۚ وَلَقَدۡ جَآءَتۡهُمۡ
رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَمَا كَانُواْ لِيُؤۡمِنُواْ بِمَا كَذَّبُواْ مِن قَبۡلُۚ كَذَٰلِكَ يَطۡبَعُ ٱللَّهُ عَلَىٰ قُلُوبِ
ٱلۡكَٰفِرِينَ ١٠١ وَمَا وَجَدۡنَا لِأَكۡثَرِهِم مِّنۡ عَهۡدٖۖ وَإِن وَجَدۡنَآ أَكۡثَرَهُمۡ لَفَٰسِقِينَ ١٠٢

**94-102.** በየትኛውም ከተማ (ይዋደቁ) ለአላህ ይተናነሱ ዘንድ በድህነትና በችግር የያዝናቸው ብንሆን እንጂ አንድንም ነብይ አልላክንም። ከዚያም እስከበዙና አባቶቻችን ድህነትና በሽታ ነክቷቸው ነበር ይኸም የጊዜ ልማድ ነው እስካሉ ድረስ በመጥፎው ስፍራ በጎውን ለወጥን። ከዚያ ወዲያው የማያውቁ ሆነው በድንገት አጠፋናቸው። የከተሞቹ ሰዎችም ባመኑና በተጠነቀቁ ኖሮ በእነርሱ ላይ ከሰማይና ከምድር በረከቶችን በከፈትንላቸው ነበር። ግን አስተባበሉ። ይሠሩት በነበሩትም ኃጢአት ምክኒያት ቀጣናቸው። የከተሞቹ ሰዎች እነሱ የተኙ ሆነው ቅጣታችን ሌሊት ሊመጣባቸው አይፈሩምን? (ተማመኑን?) የከተሞቹ ሰዎች እነሱ የሚጫወቱ ሆነው ሳሉ ቅጣታችን ቀን በረፋዱ ሊመጣባቸው አይፈሩምን? (ተማመኑን?) የአላህን ማዘናጋት (ብቀላ) አይፈሩምን? ተማመኑን? የአላህን ማዘናጋት (ብቀላ) ከከሳሪዎች ሕዝቦች በስተቀር ማንም የሚተማመን የለም። ለእነዚያ ምድርን ከባለቤቶችዋ ጥፋት በኋላ ለሚወርሱት ብንሻ (ብንፈልግ) ኖሮ በኃጢአቶቻቸው ምክኒያት የምንቀጣቸው መሆናችን አልተገለፀላቸውምን? በልቦቻቸው ላይ እናትማለን። ስለዚህም እነርሱ አይሰሙም። እነዚህ ከተሞች ከነብዩ ኑሕ እስከ ነብዩ ሹዓይብ ሰዎች የተነገሩት ከወሬዎቻቸው በአንተ ላይ እንተርካለን። መልዕክተኞቻቸውም በግልጽ ተዓምራት መጥተውላቸዋል። ከመምጣታቸው በፊት ባስተባበሉትም ነገር የሚያምኑ አልሆነም። ልክ እንደዚሁ አላህ በከሓዲያን ልቦች ላይ ያትማል። ለብዙዎቻቸው በቃል ኪዳናቸው መሙላትን አላገኘንም። አብዛኞቻቸውን ይልቁንም አመፀኞች ሆነው አገኘናቸው።

ثُمَّ بَعَثْنَا مِنۢ بَعْدِهِم مُّوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ وَمَلَإِيْهِۦ فَظَلَمُوا۟ بِهَاۖ فَٱنظُرْ كَيْفَ كَانَ
عَٰقِبَةُ ٱلْمُفْسِدِينَ ﴿١٠٣﴾ وَقَالَ مُوسَىٰ يَٰفِرْعَوْنُ إِنِّى رَسُولٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٠٤﴾ حَقِيقٌ
عَلَىٰٓ أَن لَّآ أَقُولَ عَلَى ٱللَّهِ إِلَّا ٱلْحَقَّۚ قَدْ جِئْتُكُم بِبَيِّنَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ فَأَرْسِلْ مَعِىَ بَنِىٓ
إِسْرَٰٓءِيلَ ﴿١٠٥﴾ قَالَ إِن كُنتَ جِئْتَ بِـَٔايَةٍ فَأْتِ بِهَآ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴿١٠٦﴾ فَأَلْقَىٰ
عَصَاهُ فَإِذَا هِىَ ثُعْبَانٌ مُّبِينٌ ﴿١٠٧﴾ وَنَزَعَ يَدَهُۥ فَإِذَا هِىَ بَيْضَآءُ لِلنَّٰظِرِينَ ﴿١٠٨﴾ قَالَ ٱلْمَلَأُ
مِن قَوْمِ فِرْعَوْنَ إِنَّ هَٰذَا لَسَٰحِرٌ عَلِيمٌ ﴿١٠٩﴾ يُرِيدُ أَن يُخْرِجَكُم مِّنْ أَرْضِكُمْۖ فَمَاذَا
تَأْمُرُونَ ﴿١١٠﴾ قَالُوٓا۟ أَرْجِهْ وَأَخَاهُ وَأَرْسِلْ فِى ٱلْمَدَآئِنِ حَٰشِرِينَ ﴿١١١﴾ يَأْتُوكَ بِكُلِّ سَٰحِرٍ

عَلِيمٖ ﴿١١٢﴾ وَجَآءَ ٱلسَّحَرَةُ فِرۡعَوۡنَ قَالُوٓاْ إِنَّ لَنَا لَأَجۡرًا إِن كُنَّا نَحۡنُ ٱلۡغَٰلِبِينَ ﴿١١٣﴾ قَالَ نَعَمۡ
وَإِنَّكُمۡ لَمِنَ ٱلۡمُقَرَّبِينَ ﴿١١٤﴾ قَالُواْ يَٰمُوسَىٰٓ إِمَّآ أَن تُلۡقِيَ وَإِمَّآ أَن نَّكُونَ نَحۡنُ ٱلۡمُلۡقِينَ ﴿١١٥﴾
قَالَ أَلۡقُواْۖ فَلَمَّآ أَلۡقَوۡاْ سَحَرُوٓاْ أَعۡيُنَ ٱلنَّاسِ وَٱسۡتَرۡهَبُوهُمۡ وَجَآءُو بِسِحۡرٍ عَظِيمٖ ﴿١١٦﴾
۞وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنۡ أَلۡقِ عَصَاكَۖ فَإِذَا هِيَ تَلۡقَفُ مَا يَأۡفِكُونَ ﴿١١٧﴾ فَوَقَعَ ٱلۡحَقُّ وَبَطَلَ
مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿١١٨﴾ فَغُلِبُواْ هُنَالِكَ وَٱنقَلَبُواْ صَٰغِرِينَ ﴿١١٩﴾ وَأُلۡقِيَ ٱلسَّحَرَةُ سَٰجِدِينَ ﴿١٢٠﴾
قَالُوٓاْ ءَامَنَّا بِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٢١﴾ رَبِّ مُوسَىٰ وَهَٰرُونَ ﴿١٢٢﴾

**103-122.** ከዚያ ከበኋላቸው ነብዩ ሙሳን ወደ ፈርኦንና ወደ መማከርቶቹ ተዐምራታችንን አስይዘን ላክነው። በእርሷም ካዱ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የአጥፊዎች መጨረሻ እንዴት እንደነበረ እስቲ ተመልከት። ሙሳም፡- ፈርኦን! ሆይ እኔ ከዓለማት ጌታ የተላክሁ መልክተኛ ነኝ? አለ። በአላህ ላይ ከእውነት በቀር አለመናገር ተገቢዬ ነው። ከጌታችሁ ተዐምር ይዤ መጥቻለሁና የኢስራኤል ልጆችን ከእኔ ጋር ልቀቅ አለ። ፈርኦንም፡ በተዐምር የመጣህ ከሆንክና ከእውነተኞቹ ከሆንክ እስቲ አምጣት አለው። ሙሳም ዘንጉን ምድር ላይ ጣለ። እርሷም ወዲያውኑ ግልጽ እባብ ሆነች። እጁንም አወጣ። እርሷም ወዲያውኑ ለተመልካቾች ነጭ ሆነች። ከፈርኦን ሰዎች መማከርቶቹ፡ ይህ በእርግጥ ዐዋቂ ድግምተኛ ነው አሉ። ከምድራችሁ ሊያወጣችሁ ይሻል (አሉ)። ታዲያ ምን ታዛላችሁ? አለ። እነርሱም እርሱንና ወንድሙን አቆያቸው። ወደ ከተሞቹ ሁሉ ሰብሳቢዎችን ላክ። አዋቂ ድግምተኞችን ሁሉ ያመጡልሃልና አሉ። ድግምተኞቹም ወደ ፈርኦን መጡና እኛ አሸናፊዎች ብንሆን ለኛ ክፍያ አለን? አሉ። ፈርአውንም አዎን እናንተ እኔ ዘንድ ከባለሟሎቹ ትሆናላችሁ አላቸው። እነርሱም ሙሳ ሆይ! ዘንግህን በፊት ትጥላለህ ወይም ፊት እኛ ጣዮች እንሆናለን አሉት። ሙሳም በፊት ጣሉ አላቸው። ከዚያ ገመዶቻቸውን በጣሉ ጊዜ የሰዎቹን ዓይኖች ደገሙባቸውና አስፈራሯቸውም። ትልቅ ድግምትንም አመጡ። ወደ ሙሳም ዘንግህን ጣል ስንል ላክንበት (ጣላትም) ወዲውኑም የሚቀጠጥፉትን ማታለያ ሁሉ መዋጥ ጀመረች። እውነቱም ተገለፀ። ይሠሩት የነበሩት ድግምትም ተበላሸ። እዚያ ላይ ተሸነፉና ወራዶች ሆነው ተመለሱ። ድግምተኞቹም ሰጋጆች ሆነው ሱጁድ ወረዱ። በዓለማት ጌታ አመን አሉ። በሙሳና በሃሩን ጌታ።

قَالَ فِرۡعَوۡنُ ءَامَنتُم بِهِۦ قَبۡلَ أَنۡ ءَاذَنَ لَكُمۡۖ إِنَّ هَٰذَا لَمَكۡرٞ مَّكَرۡتُمُوهُ فِي ٱلۡمَدِينَةِ
لِتُخۡرِجُواْ مِنۡهَآ أَهۡلَهَاۖ فَسَوۡفَ تَعۡلَمُونَ ﴿١٢٣﴾ لَأُقَطِّعَنَّ أَيۡدِيَكُمۡ وَأَرۡجُلَكُم مِّنۡ خِلَٰفٖ
ثُمَّ لَأُصَلِّبَنَّكُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿١٢٤﴾ قَالُوٓاْ إِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا مُنقَلِبُونَ ﴿١٢٥﴾ وَمَا تَنقِمُ مِنَّآ إِلَّآ أَنۡ ءَامَنَّا
بِـَٔايَٰتِ رَبِّنَا لَمَّا جَآءَتۡنَاۚ رَبَّنَآ أَفۡرِغۡ عَلَيۡنَا صَبۡرٗا وَتَوَفَّنَا مُسۡلِمِينَ ﴿١٢٦﴾ وَقَالَ ٱلۡمَلَأُ مِن
قَوۡمِ فِرۡعَوۡنَ أَتَذَرُ مُوسَىٰ وَقَوۡمَهُۥ لِيُفۡسِدُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَيَذَرَكَ وَءَالِهَتَكَۚ قَالَ سَنُقَتِّلُ
أَبۡنَآءَهُمۡ وَنَسۡتَحۡيِۦ نِسَآءَهُمۡ وَإِنَّا فَوۡقَهُمۡ قَٰهِرُونَ ﴿١٢٧﴾ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوۡمِهِ ٱسۡتَعِينُواْ بِٱللَّهِ
وَٱصۡبِرُوٓاْۖ إِنَّ ٱلۡأَرۡضَ لِلَّهِ يُورِثُهَا مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦۖ وَٱلۡعَٰقِبَةُ لِلۡمُتَّقِينَ ﴿١٢٨﴾ قَالُوٓاْ
أُوذِينَا مِن قَبۡلِ أَن تَأۡتِيَنَا وَمِنۢ بَعۡدِ مَا جِئۡتَنَاۚ قَالَ عَسَىٰ رَبُّكُمۡ أَن يُهۡلِكَ عَدُوَّكُمۡ
وَيَسۡتَخۡلِفَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَيَنظُرَ كَيۡفَ تَعۡمَلُونَ ﴿١٢٩﴾

**123-129.** ፈርኦን እኔ ለእናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት በእርሱ አመናችሁን? ይህ በከተማይቱ ውስጥ ሰውን ከእርሷ ለማውጣት የተስማማችሁበት ተንኮል ነው። ወደፊት የሚደርስባችሁን ታውቃላችሁ አለ። እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማፈራረቅ በእርግጥ እቆራርጣለሁ። ከዚያ ሁላችሁንም በእርግጥ እሰቅላችኋለሁ። እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን። የጌታችንም ተዐምራቶች በመጡልን ጊዜ ከማመናችን በቀር ከእኛ አትጠላም። ጌታችን ሆይ! በእኛ ላይ ትዕግስትን አፍስስ። ሙስሊሞችም ሆነን ግደለን አሉ። ከፈርኦን ሰዎች ታላላቆቹ ለፈርኦን ሙሳንና ሰዎችን በምድር ላይ እንዲያበላሹና ሙሳም አንተንና አማልክቶችህን እንዲተው ትተዋቸዋለህን? አሉ። እሱም ወንዶች ልጆቻቸውን እንገድላለን ሴቶቻቸውንም እናስቀራለን። እኛም ከበላያቸው ነን አሸናፊዎች ነን አለ። ሙሳ ለሰዎቹ፡- አላህን ተገዙ። ታገሱም። ምድር ለአላህ ናትና ከባሮቹ መካከል ለሚሻው ያወርሳታል። ምስጉንዋም ፍጻሜ ለጥንቁቆቹ ብቻ ናት አላቸው። አንተ ከመምጣትህ በፊትም ሆነ ከመጣህልን በኋላ ተሰቃየን አሉት። ጌታችሁ ጠላቶቻችሁን ሊያጠፋና እንዴት እንደምትሰሩ ይመለከት ዘንድ በምድር ላይ ሊተካችሁ ይፈልጋል አላቸው።

وَلَقَدۡ أَخَذۡنَآ ءَالَ فِرۡعَوۡنَ بِٱلسِّنِينَ وَنَقۡصٖ مِّنَ ٱلثَّمَرَٰتِ لَعَلَّهُمۡ يَذَّكَّرُونَ ﴿١٣٠﴾ فَإِذَا
جَآءَتۡهُمُ ٱلۡحَسَنَةُ قَالُواْ لَنَا هَٰذِهِۦۖ وَإِن تُصِبۡهُمۡ سَيِّئَةٞ يَطَّيَّرُواْ بِمُوسَىٰ وَمَن مَّعَهُۥٓۗ أَلَآ إِنَّمَا

طَٰٓئِرُهُمۡ عِندَ ٱللَّهِ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ١٣١ وَقَالُواْ مَهۡمَا تَأۡتِنَا بِهِۦ مِنۡ ءَايَةٖ
لِّتَسۡحَرَنَا بِهَا فَمَا نَحۡنُ لَكَ بِمُؤۡمِنِينَ ١٣٢ فَأَرۡسَلۡنَا عَلَيۡهِمُ ٱلطُّوفَانَ وَٱلۡجَرَادَ وَٱلۡقُمَّلَ
وَٱلضَّفَادِعَ وَٱلدَّمَ ءَايَٰتٖ مُّفَصَّلَٰتٖ فَٱسۡتَكۡبَرُواْ وَكَانُواْ قَوۡمٗا مُّجۡرِمِينَ ١٣٣ وَلَمَّا وَقَعَ
عَلَيۡهِمُ ٱلرِّجۡزُ قَالُواْ يَٰمُوسَى ٱدۡعُ لَنَا رَبَّكَ بِمَا عَهِدَ عِندَكَۖ لَئِن كَشَفۡتَ عَنَّا ٱلرِّجۡزَ
لَنُؤۡمِنَنَّ لَكَ وَلَنُرۡسِلَنَّ مَعَكَ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ١٣٤ فَلَمَّا كَشَفۡنَا عَنۡهُمُ ٱلرِّجۡزَ إِلَىٰٓ أَجَلٍ هُم
بَٰلِغُوهُ إِذَا هُمۡ يَنكُثُونَ ١٣٥ فَٱنتَقَمۡنَا مِنۡهُمۡ فَأَغۡرَقۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡيَمِّ بِأَنَّهُمۡ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا
وَكَانُواْ عَنۡهَا غَٰفِلِينَ ١٣٦ وَأَوۡرَثۡنَا ٱلۡقَوۡمَ ٱلَّذِينَ كَانُواْ يُسۡتَضۡعَفُونَ مَشَٰرِقَ ٱلۡأَرۡضِ
وَمَغَٰرِبَهَا ٱلَّتِي بَٰرَكۡنَا فِيهَاۖ وَتَمَّتۡ كَلِمَتُ رَبِّكَ ٱلۡحُسۡنَىٰ عَلَىٰ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ بِمَا صَبَرُواْۖ
وَدَمَّرۡنَا مَا كَانَ يَصۡنَعُ فِرۡعَوۡنُ وَقَوۡمُهُۥ وَمَا كَانُواْ يَعۡرِشُونَ ١٣٧

**130-137.** የፈርኦንንም ቤተሰቦች እንዲገሰፁ በድርቅና የፍራፍሬ ምርታቸውን በመቀነስ በእርግጥ ቀጣናቸው። ምቾት በመጣላቸው ጊዜ ይህ ለእኛ ተገቢ ነው ይላሉ። ክፋት ባገኛቸው ጊዜ ግን ሙሳና አብረውት ያሉ አማኞች ክፉ ገዶቻቸው እንዲሆኑ ያስባሉ። አማኞች ሆይ አስተውሉ! ክፉ እድላቸው (ገደቢስነታቸው) ከአላህ ዘንድ ነው። አብዛኞቻቸው ይህን አያውቁም። ለሙሳም በማንኛይቱም ተዐምር በእርሷ ልትደግምብን ብታመጣብን እኛ ለአንተ የምናምንልህ አይደለንም አሉ። ወዲያውም የውሃን ማጥለቅለቅ፤ አንበጣንም፤ ነቀዝንም፤ እንቁራሪቶችንም፤ ደምንም፤ የተለያዩ ተዐምራት ሲሆኑ በእነርሱ ላይ ላክን። እነርሱ ግን ኮሩም። ተንኮለኞችም ህዝቦች ነበሩ። በእነርሱ ላይ ቅጣቱ በወደቀባቸው ጊዜ ሙሳ ሆይ! ጌታህን ላንተ ቃል ኪዳን በገባልህ መሠረት ለምንልንና ከእኛ ቅጣቱን ብታነሳልን እናምንልሀለን የኢስራኤልን ልጆችም ካንተ ጋር እንለቃለን አሉ። እነርሱም ለሚደርሱበት የተወሰነ ጊዜ ድረስ ቅጣትን ከእነርሱ ላይ ባነሳን ጊዜ ወዲያውኑ እነርሱ ቃላቸውን ያፈርሳሉ። እነርሱ በተዐምራታችን ስላስተባበሉና ከእርሷ ዘንጊዎች ስለሆኑ ከእነሱ ተበቀልናቸው። በባህር ውስጥም አሰመጥናቸው። እነዚያን ደካሞች የነበሩትን ህዝቦች ያቺን በውስጧ በረከት ያደረግንባትን ምድር ምስራቁንም ምዕራቡንም አወረስናቸው። (መልዕክተኛችን ሆይ!) የጌታህ መልካሚቱ ቃል በኢስራኤል ልጆች ላይ በመታገላቸው ተፈፀመች። ፈርኦንና ሰወቹም ይሰሩት የነበረውን ህንጻና ዳስ ያደረጉት የነበረውንም አፈረስን።

**ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (90-137) ከምናገኛቸው አንኳር ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ በቀደምት ነብያት ሕዝቦች ላይ ያደረሰውን በማስታወስ ትምህርት መቅሰም ያለውን ጠቀሜታ የቁረይሽ ጣኦታዊያን ከነዚህ ሕዝቦች ሁኔታ ትምህርት በመውሰድ እምነታቸውን ማስተካከል ይገባቸው እንደነበር የተላለፈ ቁርኣናዊ ምክር መኖሩን፤
2. የአላህ ረድኤትን ለማግኘት የሚሻ ሰው እምነት ና የእርሱን ፍራቻ ከልቡ ማሳደር የሚገባው መሆኑን፤
3. ከኢስላማዊ ትዕዛዛት መዘናጋት ለውድቀት የሚዳርግ በመሆኑ ንቃትን መላበሱ ተገቢ ስለመሆኑ፤
4. የአላህን ቅጣት አይደርስብኝም ብሎ በሙሉ ልብ መተማመን ያለውን መጥፍ ጎን፤
5. ያለፉት ሕዝቦች በወንጀላቸው ምክንያት ከደረሰባቸው ምድራዊ ቅጣት መማር ግዴታ ስለመሆኑ፤
6. በነብዩ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ቁርኣናዊ አንቀፅና መልዕክት እንደወረደላቸው፤
7. ጠንካራ ማስረጃዎችን ተንተርሶ የሚሰጡ ትምህርቶችን ቢያገኝም ከአላህ መመራት ያልተሰጠው ሰው እምነትን እንደማይዝ፤
8. ፊርአውን እና ተከታዮቹ ሙሳን «ድግምተኛ ነው» ሲሉ መወንጀላቸውንና ስማቸውን በሀሰት ማጥፋታቸውን፤
9. ፊርኦን «እኔ የአለማት ጌታ ነኝ» ሲል የሀሰት ፕሮፖጋንዳውን ቢነዛም ተራ ሰው መሆኑን የሚያጋልጡበት ሥራዎችን ሲተገብር ይታይ እንደነበርና ጭንቅ ሲለው ባልደረቦቹን ምን ቢያደርግ እንደሚሻለው ማማከሩ የአቅሙን ደካማነት የሚያጋልጥ መሆኑን፤
10. ድግምት እንደማንኛውም ሙያዎች በትምህርት ሊገኝ የሚችል ሙያ መሆኑንና ድግምትን መማርም ሆነ መተግባሩ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
11. ማንኛውም ሰው ለሰራው ሥራና ለድካሙ ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ መጠየቅ የሚችል ስለ መሆኑ፤
12. ድግምት በሰዎች እይታ ላይ ተፅእኖ ሊያደርግ የሚችል ስለመሆኑ፤
13. እውነትና ሐሰት በሚያደርጉት መፋተግና ጦርነት ምንጊዜም በእውነት ድል አድራጊነት እንደሚጠናቀቅ፤
14. ልቦናቸውን ለኩፍርና ለሽርክ የከፈቱ ከሓዲያን ውሸትን ከመናገር፤ በሐሰት ንፁሃንን ከመወንጀልና ሌሎችንም ወንጀሎች ከመስራት ወደኋላ የማይሉ መሆናቸውን፤
15. የግፈኞች ዛቻ ሲበረታ ወደ አላህ መጠጋት ተወዳጅ ስለ መሆኑ፤
16. በእምነት ላይ ሙሉ ፅናትን ለመጎናጸፍ የሚቻለው በአላህ እርዳታ መሆኑን፤
17. ፅናትን ከርሱ መለመን አስፈላጊነቱንና እስከ እለተ ሞት ድረስ እምነትን በሙሉ ፅናት ማራመድ ያለውን ከፍተኛ ምንዳ፤ እንመነዳለን።
18. እውቀት መመራት ትልቅ የመግቢያ በር እንደሚሆን፤
19. የአላህን ውሳኔን የሚሽር ምንም ኃይል እንደሌለና ምንም ነገር በራሱ ፍላጎት ብቻ እንደሚመራ ከሚያሳዩ ተጨባጭ ማስረጃዎች መሀከል የሁኔታዎች በሰዓት ልዩነት መለዋወጥና ጠዋት ከሃዲ የነበሩ ሰዎች ከሰዓት በኋላ እምነት ሲቀበሉ መታየቱ ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን፤
20. ወደ መጥፎ ጐዳና የሚመሩ መጥፎ አማካሪዎች የሕይወትን መስመር የሚያበላሹ አደገኛ ሰዎች መሆናቸውን፤

21. ትዕግሥትና የአላህ ፍራቻ መጨረሻቸው የሚያምር ተወዳጅ ሥነ ምግባር ስለመሆናቸው፤
22. በተለያዩ ሕገ ወጥ ተግባራት የተበላሸን በሽተኛ መንፈስ ለማከም እጅግ በጣም ከባድ ቢሆንም ትእግስትና ፅናትን የሰነቀ አስተማሪ የተበላሸን መንፈስ ሊያድን የሚያስችል ብቃት እንደሚኖረው፤
23. ሙሳ ከአላህ አገኘዋለሁ ብለው ተስፋ ያደረጉበትን ነገር በተጨባጭ ማግኘታቸውንና አላህ የሙሳን ተስፋ በመሙላት ያሳየውን ውጤት፤
24. አማኞች መጨረሻቸው የሚያምር የወደፊት ተስፋቸው የለመለመ ተድላና ደስታ የሚጠብቃቸው መሆኑን እያስታወሱ ሞራላቸውን ማነሳሳትና ማበረታት ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

وَجَٰوَزۡنَا بِبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱلۡبَحۡرَ فَأَتَوۡاْ عَلَىٰ قَوۡمٖ يَعۡكُفُونَ عَلَىٰٓ أَصۡنَامٖ لَّهُمۡۚ قَالُواْ يَٰمُوسَى ٱجۡعَل
لَّنَآ إِلَٰهٗا كَمَا لَهُمۡ ءَالِهَةٞۚ قَالَ إِنَّكُمۡ قَوۡمٞ تَجۡهَلُونَ ١٣٨ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ مُتَبَّرٞ مَّا هُمۡ فِيهِ وَبَٰطِلٞ مَّا
كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٣٩ قَالَ أَغَيۡرَ ٱللَّهِ أَبۡغِيكُمۡ إِلَٰهٗا وَهُوَ فَضَّلَكُمۡ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٤٠

**138-140.** የኢስራኤል ልጆችን ባህሩን አሻገርናቸው። ለእነርሱም ጣኦታትን መገዛት ላይ በሚዘወትሩ ህዝቦች አጠገብ አለፉም። ሙሳ ሆይ! ለእነርሱ ለሰዎቹ አማልክት እንዳሏቸው ሁሉ ለኛም አምላክን አድርግልን አሉት። እናንተ የምትሳሳቱ ህዝቦች ናችሁ አላቸው። እነዚህ በውስጡ ያሉበት ነገር ጠፊ ነው። ይሰሩት የነበሩትም ብልሹ ነው አላቸው። ከአላህ ሌላ እሱ ከዓለማት ያበለጣችሁ ሲሆን የምትገዙት አምላክን እፈልግላችኋለሁን? አለ።

وَإِذۡ أَنجَيۡنَٰكُم مِّنۡ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ يَسُومُونَكُمۡ سُوٓءَ ٱلۡعَذَابِ يُقَتِّلُونَ أَبۡنَآءَكُمۡ وَيَسۡتَحۡيُونَ
نِسَآءَكُمۡۚ وَفِي ذَٰلِكُم بَلَآءٞ مِّن رَّبِّكُمۡ عَظِيمٞ ١٤١ ۞ وَوَٰعَدۡنَا مُوسَىٰ ثَلَٰثِينَ لَيۡلَةٗ
وَأَتۡمَمۡنَٰهَا بِعَشۡرٖ فَتَمَّ مِيقَٰتُ رَبِّهِۦٓ أَرۡبَعِينَ لَيۡلَةٗۚ وَقَالَ مُوسَىٰ لِأَخِيهِ هَٰرُونَ ٱخۡلُفۡنِي فِي
قَوۡمِي وَأَصۡلِحۡ وَلَا تَتَّبِعۡ سَبِيلَ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ١٤٢

**141-142.** (የኢስራኤል ልጆች ሆይ)፣ ከፈርኦንም ቤተሰቦች ብርቱን ቅጣት የሚያቀምሷችሁ ወንዶች ልጆቻችሁን የሚገድሉ ሴቶቻችሁን የሚተው ሲሆኑ ባዳንናችሁ ጊዜ አስታውሱ። በዚህ ውስጥ ከጌታችሁ የሆነ ከባድ ፈተና አለበት። ነብዩ ሙሳን ሰላሳን ሌሊት ሊፆምና ልናነጋግረው ቀጠርነው። በአስርም ሌሊት ሞላናት። የጌታውም ቀጠሮ አርባ ሌሊት ሲሆን ተፈፀመ። ሙሳም ለወንድሙ ለነብዩ ሀሩን በህዝቦቼ ላይ ተተካኝና አሳምር። የአጥፊዎችን መንገድ አትከተል አለው።

وَلَمَّا جَآءَ مُوسَىٰ لِمِيقَٰتِنَا وَكَلَّمَهُۥ رَبُّهُۥ قَالَ رَبِّ أَرِنِيٓ أَنظُرۡ إِلَيۡكَۚ قَالَ لَن تَرَىٰنِي وَلَٰكِنِ
ٱنظُرۡ إِلَى ٱلۡجَبَلِ فَإِنِ ٱسۡتَقَرَّ مَكَانَهُۥ فَسَوۡفَ تَرَىٰنِيۚ فَلَمَّا تَجَلَّىٰ رَبُّهُۥ لِلۡجَبَلِ جَعَلَهُۥ دَكّٗا
وَخَرَّ مُوسَىٰ صَعِقٗاۚ فَلَمَّآ أَفَاقَ قَالَ سُبۡحَٰنَكَ تُبۡتُ إِلَيۡكَ وَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿١٤٣﴾ قَالَ
يَٰمُوسَىٰٓ إِنِّي ٱصۡطَفَيۡتُكَ عَلَى ٱلنَّاسِ بِرِسَٰلَٰتِي وَبِكَلَٰمِي فَخُذۡ مَآ ءَاتَيۡتُكَ وَكُن مِّنَ
ٱلشَّٰكِرِينَ ﴿١٤٤﴾ وَكَتَبۡنَا لَهُۥ فِي ٱلۡأَلۡوَاحِ مِن كُلِّ شَيۡءٖ مَّوۡعِظَةٗ وَتَفۡصِيلٗا لِّكُلِّ شَيۡءٖ فَخُذۡهَا
بِقُوَّةٖ وَأۡمُرۡ قَوۡمَكَ يَأۡخُذُواْ بِأَحۡسَنِهَاۚ سَأُوْرِيكُمۡ دَارَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ﴿١٤٥﴾ سَأَصۡرِفُ عَنۡ ءَايَٰتِيَ
ٱلَّذِينَ يَتَكَبَّرُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّ وَإِن يَرَوۡاْ كُلَّ ءَايَةٖ لَّا يُؤۡمِنُواْ بِهَا وَإِن يَرَوۡاْ سَبِيلَ
ٱلرُّشۡدِ لَا يَتَّخِذُوهُ سَبِيلٗا وَإِن يَرَوۡاْ سَبِيلَ ٱلۡغَيِّ يَتَّخِذُوهُ سَبِيلٗاۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ كَذَّبُواْ
بِـَٔايَٰتِنَا وَكَانُواْ عَنۡهَا غَٰفِلِينَ ﴿١٤٦﴾ وَٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَلِقَآءِ ٱلۡأٓخِرَةِ حَبِطَتۡ أَعۡمَٰلُهُمۡۚ
هَلۡ يُجۡزَوۡنَ إِلَّا مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿١٤٧﴾

**143-147.** ሙሳ ለቀጠሮው በመጣና ጌታውም ባነጋገረው ጊዜ፡ ጌታዬ ሆይ! አንተን አሳየኝ ወደ አንተ እመለከታለሁና አለ። አላህም፡- እኔን በፍፁም አታየኝም። ግን ወደ ተራራው ተመልከትና በስፍራው ከረጋ አንተም ታየኛለህ አለው። ጌታውም ለተራራው በተገለፀ ጊዜ እንኩትኩት አደረገው። ሙሳም ጮኸና ወደቀ። በአንሰራራም ጊዜ ጌታዬ ጥራት ይገባህ ወደ አንተ ተመለስኩ። እኔም በጊዜያቴ የምዕመናን መጀመሪያ ነኝ አለ። አላህም አለ፡- ሙሳ ሆይ! እኔ በመልዕክቶቼና በማናገሬ በሰዎች ላይ መረጥኩህ የሰጠሁህንም ያዝ ከአመስጋኞችም ሁን አለው። ለእርሱም በሰሌዳዎቹ ላይ ከሁሉ ነገር ግሳጼንና ለሁሉ ነገር ማብራራትን ጻፍንለትና አልንም በብርታትም ያዛት ሕዝቦችህንም በመልካሟ እንዲይዙ እዘዛቸው የአመፀኞቹን አገር በእርግጥ አሳያችኋለሁ። እነዚያን ያለ አግባብ በምድር ላይ የሚኮሩትን ከአንቀጾቼ በእርግጥ አዞራቸዋለሁ። ተዓምርንም ሁሉ ቢያዩ በእርሷ አያምኑም። ቅንንም መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው አይዙትም። ግን የጥመትን መንገድ ቢያዩ መንገድ አድርገው ይይዙታል። ይህ እነርሱ በአንቀፆቻችው ስለ አስተባበሉና ከእርሷም ዘንጊዎች ስለሆኑ ነው። እነዚያም በአንቀፆቻችንና መጨረሻይቱን ዓለም በመገናኘት ያስተባበሉት ሥራዎቻቸው ተበላሹ። ይሰሩት የነበረውን እንጂ ይመነዳሉን?

وَٱتَّخَذَ قَوۡمُ مُوسَىٰ مِنۢ بَعۡدِهِۦ مِنۡ حُلِيِّهِمۡ عِجۡلٗا جَسَدٗا لَّهُۥ خُوَارٌۚ أَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّهُۥ
لَا يُكَلِّمُهُمۡ وَلَا يَهۡدِيهِمۡ سَبِيلًاۘ ٱتَّخَذُوهُ وَكَانُواْ ظَٰلِمِينَ ﴿١٤٨﴾ وَلَمَّا سُقِطَ فِيٓ أَيۡدِيهِمۡ وَرَأَوۡاْ
أَنَّهُمۡ قَدۡ ضَلُّواْ قَالُواْ لَئِن لَّمۡ يَرۡحَمۡنَا رَبُّنَا وَيَغۡفِرۡ لَنَا لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ﴿١٤٩﴾

**148-149.** የሙሳም ህዝቦች ከእርሱ መሄድ በኋላ ከጌጦቻቸው በወይፈን ቅርፅ የተቀረፀውን እና የራሱ የሆነ ድምፅ የነበረውን አካል አምላክ አድርገው ያዙ። እርሱ የማያናግራቸው መንገድን የማይመራቸው መሆኑን አይመለከቱምን? አምላክ አድርገው ያዙት። በዳዮችም ሆኑ። በተፀፀቱና እነርሱም በእርግጥ የተሳሳቱ መሆናቸውን ባዩ ጊዜ ጌታችን ባያዝንልንና ባይምረን ኖሮ በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን አሉ።

وَلَمَّا رَجَعَ مُوسَىٰٓ إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ غَضۡبَٰنَ أَسِفٗا قَالَ بِئۡسَمَا خَلَفۡتُمُونِي مِنۢ بَعۡدِيٓۖ أَعَجِلۡتُمۡ
أَمۡرَ رَبِّكُمۡۖ وَأَلۡقَى ٱلۡأَلۡوَاحَ وَأَخَذَ بِرَأۡسِ أَخِيهِ يَجُرُّهُۥٓ إِلَيۡهِۚ قَالَ ٱبۡنَ أُمَّ إِنَّ ٱلۡقَوۡمَ
ٱسۡتَضۡعَفُونِي وَكَادُواْ يَقۡتُلُونَنِي فَلَا تُشۡمِتۡ بِيَ ٱلۡأَعۡدَآءَ وَلَا تَجۡعَلۡنِي مَعَ ٱلۡقَوۡمِ
ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٥٠﴾ قَالَ رَبِّ ٱغۡفِرۡ لِي وَلِأَخِي وَأَدۡخِلۡنَا فِي رَحۡمَتِكَۖ وَأَنتَ أَرۡحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿١٥١﴾

**150-151.** ሙሳም እየተቆጣና እያዘነ ወደ ህዝቦቹ በተመለሰ ጊዜ በእኔ ቦታ የተካችሁት ነገር ከፋ። የጌታችሁን ትዕዛዝ ተቻኮላችሁን? አላቸውና ሰሌዳዎቹንም ጣላቸው የወንድሙን የራስ ፀጉር ወደ እርሱ እየጎተተው ያዘ። (ወንድሙም):- የእናቴ ልጅ ሆይ ህዝቦቹ ናቁኝ ሊገድሉኝም ተቃረቡ። ስለዚህ በእኔ ጠላቶችን አታስደስትብኝ ከአመፀኞች ህዝቦችም ጋር አታድርገኝ አለው። ሙሳም:- ጌታዬ ሆይ! ለኔም ለወንድሜንም ማረን በእዝነትህ ውስጥ አስገባን አንተም ከአዛኞቹ ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህና አለ።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ ٱلۡعِجۡلَ سَيَنَالُهُمۡ غَضَبٞ مِّن رَّبِّهِمۡ وَذِلَّةٞ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۚ وَكَذَٰلِكَ نَجۡزِي
ٱلۡمُفۡتَرِينَ ﴿١٥٢﴾ وَٱلَّذِينَ عَمِلُواْ ٱلسَّيِّـَٔاتِ ثُمَّ تَابُواْ مِنۢ بَعۡدِهَا وَءَامَنُوٓاْ إِنَّ رَبَّكَ مِنۢ بَعۡدِهَا
لَغَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿١٥٣﴾

**152-153.** እነዚያ ወይፈኑን አምላክ አድርገው የያዙት ሰዎች በሁለተኛይቱ ዓለም ከጌታቸው ዘንድ ቁጣ በቅርቢቱም ህይወት ውርደት ያገኛቸዋል ልክ እንዲዚሁ ቀጣፊዎችን እንቀጣለን። እነዚያ ኃጢአቶችን የሠሩ ከዚያ ከርሷ በኋላ የተፀፀቱና በአላህ ያመኑ ጌታህ ከእርሷ በኋላ መሀሪና አዛኝ ነው። (ፀፀታቸውን ይቀበላቸዋል)።

وَلَمَّا سَكَتَ عَن مُّوسَى ٱلْغَضَبُ أَخَذَ ٱلْأَلْوَاحَ ۖ وَفِى نُسْخَتِهَا هُدًى وَرَحْمَةٌ لِّلَّذِينَ هُمْ
لِرَبِّهِمْ يَرْهَبُونَ ﴿١٥٤﴾ وَٱخْتَارَ مُوسَىٰ قَوْمَهُۥ سَبْعِينَ رَجُلًا لِّمِيقَٰتِنَا ۖ فَلَمَّآ أَخَذَتْهُمُ ٱلرَّجْفَةُ
قَالَ رَبِّ لَوْ شِئْتَ أَهْلَكْتَهُم مِّن قَبْلُ وَإِيَّٰىَ ۖ أَتُهْلِكُنَا بِمَا فَعَلَ ٱلسُّفَهَآءُ مِنَّآ ۖ إِنْ هِىَ إِلَّا
فِتْنَتُكَ تُضِلُّ بِهَا مَن تَشَآءُ وَتَهْدِى مَن تَشَآءُ ۖ أَنتَ وَلِيُّنَا فَٱغْفِرْ لَنَا وَٱرْحَمْنَا ۖ وَأَنتَ خَيْرُ
ٱلْغَٰفِرِينَ ﴿١٥٥﴾ ۞ وَٱكْتُبْ لَنَا فِى هَٰذِهِ ٱلدُّنْيَا حَسَنَةً وَفِى ٱلْءَاخِرَةِ إِنَّا هُدْنَآ إِلَيْكَ ۚ قَالَ عَذَابِىٓ
أُصِيبُ بِهِۦ مَنْ أَشَآءُ ۖ وَرَحْمَتِى وَسِعَتْ كُلَّ شَىْءٍ ۚ فَسَأَكْتُبُهَا لِلَّذِينَ يَتَّقُونَ وَيُؤْتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ
وَٱلَّذِينَ هُم بِـَٔايَٰتِنَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٥٦﴾

**154-156.** ከሙሳም ቁጣው በበረደ ጊዜ ሰሌዳዎቹን፡፡ በግልባጫቸው ውስጥ ለእነዚያ ጌታቸውን ለሚፈሩት ሰዎች ሁሉ መምሪያና እዝነት ያለባቸው ሲሆን ያዘ፡፡ ሙሳም ከህዝቦቹ መካከል ለቀጠሯችን ሰባ ሰዎችን መረጠ፡፡ ከዚያ ብርቱ የምድር እንቅጥቃጤ በደረሰባቸው ጊዜ ሙሳ አለ፡- ጌታዬ ሆይ! ብትፈልግ ኖሮ ከአሁን በፊት ባጠፋሀቸው ነበር፡፡ እኔንም ባጠፋኸኝ ነበር፡፡ ከእኛ መሀከል ቂሎቹ በሠሩት ጥፋት ታጠፋናለህን? እርሷ (ፈተናይቱ) የአንተ ፈተና እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡ በርሷ የምትሻውን ታሳስታለህ የምትሻውንም ታቀናለህ፡፡ አንተ ረዳታችን ነህና፡፡ ለእኛ ምህረት አድርግልን እዘንልንም፡፡ አንተ ከመሀሪዎች ሁሉ በላጭ ነህና፡፡ (ጌታችን ሆይ!) ለእኛም በዚች በቅርቢቱ ዓለም መልካሟን በመጨረሻይቱም ዓለም መልካሟን ጻፍልን፡፡ እኛ ወደ አንተ ተመልሰናል ሲል ሙሳ ጌታውን ለመነ፡፡ አላህም አለ፡፡ ቅጣቴ በእርሱ ልቀጣው የምፈልገውን ሰው እቀጣበታለሁ፡፡ ችሮታዬ ከሁሉም ነገር የሰፋ ነው፡፡ ለእነዚያ ለሚጠነቀቁ ዘካንም ለሚሰጡ ለእነዚያም በአንቀፆቻችን ለሚያምኑ ሁሉ በእርግጥ እጽፋታለሁ፡፡

### ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (138-155) አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-

1. አላህ በበኒ ኢስራኢሎች ላይ የዋለውን ውለታ ብዛት ማየት፤
2. ከመጋረጃ በስተጀርባ አላህ ሙሳን እንዳናገራቸው፤
3. የአላህ ብርሃን ከሰዎች አቅም በላይ መሆኑን፤
4. ወደ አላህ መመለስ ግዴታ መሆኑን፤
5. ነብዩ ሙሳ በዘመኑ ከነበሩት ህዝቦች የበለጡ እንደነበሩ፤
6. ነብያት ሁሉም በቁርጠኝነት የአላህን ህግ የመተግበር ግዴታ እንደነበረባቸው፤
7. በአላህ ላይ መኩራራት ሰዎችን መናቅ የውርደት ምልክት የድንቁርና መንገድ መሆኑን፤
8. መጥፎ ነገሮችን ፈፅመው ከዚያ ወደ አላህ ተፀፅተው የሚመለሱ ሰዎች አላህ ሊቀበላቸው እንደሚችል፤

9. ለአላህና ለአላህ ዲን ሲባል መቆጣት ግዴታ መሆኑን፤
10. ንፁህ የሆነ ሰው ራሱን የመከላከል ግዴታ እንዳለበት፤
11. ለአላህ ጥፋትን አምነው ምህረትን ከእሱ መፈለግ ተገቢ መሆኑን፤
12. በዱንያ መቀጣት ከአኺራ ቅጣትን እንደማይታደግ፤
13. የኢስራኢል ልጆች በአላህ ላይ በሚቀጥፉት ነገርና በመሳሳታቸውም ምክንያት ውርደት እንደተከተላቸው እንማራለን።

ٱلَّذِينَ يَتَّبِعُونَ ٱلرَّسُولَ ٱلنَّبِيَّ ٱلْأُمِّيَّ ٱلَّذِى يَجِدُونَهُۥ مَكْتُوبًا عِندَهُمْ فِى ٱلتَّوْرَىٰةِ وَٱلْإِنجِيلِ يَأْمُرُهُم بِٱلْمَعْرُوفِ وَيَنْهَىٰهُمْ عَنِ ٱلْمُنكَرِ وَيُحِلُّ لَهُمُ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَيُحَرِّمُ عَلَيْهِمُ ٱلْخَبَٰٓئِثَ وَيَضَعُ عَنْهُمْ إِصْرَهُمْ وَٱلْأَغْلَٰلَ ٱلَّتِى كَانَتْ عَلَيْهِمْ ۚ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِهِۦ وَعَزَّرُوهُ وَنَصَرُوهُ وَٱتَّبَعُوا۟ ٱلنُّورَ ٱلَّذِىٓ أُنزِلَ مَعَهُۥٓ ۙ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿١٥٧﴾

**157.** ለእነዚያ ያንን እነርሱ ዘንድ በተውራትና በኢንጂል ተጽፎ የሚያገኙትን የማይጽፍና የማያነብን ነብይ የሆነውን መልዕክተኛ (ነብዩ ሙሐመድን) የሚከተሉ ለሆኑ ሁሉ (በእርግጥ እጽፋታለሁ)። በበጎ ሥራ ያዝዛቸዋል። ከክፉም ነገር ይከለክላቸዋል። መልካም ነገሮችንም ለእነርሱ ይፈቅድላቸዋል መጥፎ ነገሮችንም በነሱ ላይ እርም ያደርግባቸዋል። ከእነርሱም ላይ ሸክማቸውንና እነዚያንም በእነርሱ ላይ የነበሩትን እንደ እንዛዝላ (ይከብዱ የነበሩ ከባድ ህግጋቶች) ያነሳላቸዋል። እነዚያም በእርሱ ያመኑ፤ ያከበሩት፤ የረዱትና ያንንም ከርሱ ጋር የተወረደውን ብርሃን የተከተሉ ሁሉ እነዚያ እነርሱ ከቅጣት የሚድኑ ናቸው።

قُلْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنِّى رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيْكُمْ جَمِيعًا ٱلَّذِى لَهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ يُحْىِۦ وَيُمِيتُ ۖ فَـَٔامِنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِ ٱلنَّبِىِّ ٱلْأُمِّىِّ ٱلَّذِى يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَكَلِمَٰتِهِۦ وَٱتَّبِعُوهُ لَعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ ﴿١٥٨﴾

**158.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎች ሆይ! እኔ ወደ እናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህ መልዕክተኛ ነኝ። ያ! የሰማያትና የምድር ንግስና ለእርሱ ብቻ የሆነ ነው። እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም። አላህ ህያው ያደርጋል። ይገድላልም። በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ በሆነው መልክተኛው እመኑ። ወደ ቅኑ መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት በላቸው።

وَمِن قَوۡمِ مُوسَىٰٓ أُمَّةٞ يَهۡدُونَ بِٱلۡحَقِّ وَبِهِۦ يَعۡدِلُونَ ﴿١٥٩﴾ وَقَطَّعۡنَٰهُمُ ٱثۡنَتَيۡ عَشۡرَةَ أَسۡبَاطًا
أُمَمٗاۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ إِذِ ٱسۡتَسۡقَىٰهُ قَوۡمُهُۥٓ أَنِ ٱضۡرِب بِّعَصَاكَ ٱلۡحَجَرَۖ فَٱنۢبَجَسَتۡ مِنۡهُ
ٱثۡنَتَا عَشۡرَةَ عَيۡنٗاۖ قَدۡ عَلِمَ كُلُّ أُنَاسٖ مَّشۡرَبَهُمۡۚ وَظَلَّلۡنَا عَلَيۡهِمُ ٱلۡغَمَٰمَ وَأَنزَلۡنَا عَلَيۡهِمُ ٱلۡمَنَّ
وَٱلسَّلۡوَىٰۖ كُلُواْ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقۡنَٰكُمۡۚ وَمَا ظَلَمُونَا وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ يَظۡلِمُونَ ﴿١٦٠﴾

**159-160.** ከሙሳም ህዝቦች መካከል በእውነት የሚመሩና በእውነት ፍርድን የሚያስተካከሉ ቡድኖች አሉ። የሙሳን ህዝቦች አስራ ሁለት ነገዶች አድርገን ከፋፈልናቸው። ወደ ሙሳም ወገኖቹ ውሃን በፈለጉበት ጊዜ ድንጋዩን በበትርህ ምታው ስንል ላክን። መታውም ከእርሱ አስራ ሁለት ምንጮች ፈለቁ። ሰዎቹ ሁሉ መጠጫቸውን በእርግጥ አወቁ። በእነርሱም ላይ ዳመናን አጠለልን። በእነርሱም ላይ መናን* እና ድርጭትን አወረድን። ከሰጠናችሁም መልካም ሲሳይ ብሉ (አልን)። ፀጋዎቻችንን በመካዳቸው አልበደሉንም። ግን ነፍሶቻቸውን የሚበድሉ ህዝቦች ነበሩ።

* መን ማለት በመልኩና በይዘቱ ሙጫ የሚመስል በጣዕሙ እንደ ማር ያለ ነው።

وَإِذۡ قِيلَ لَهُمُ ٱسۡكُنُواْ هَٰذِهِ ٱلۡقَرۡيَةَ وَكُلُواْ مِنۡهَا حَيۡثُ شِئۡتُمۡ وَقُولُواْ حِطَّةٞ وَٱدۡخُلُواْ ٱلۡبَابَ
سُجَّدٗا نَّغۡفِرۡ لَكُمۡ خَطِيٓـَٰٔتِكُمۡۚ سَنَزِيدُ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿١٦١﴾ فَبَدَّلَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ مِنۡهُمۡ قَوۡلًا
غَيۡرَ ٱلَّذِي قِيلَ لَهُمۡ فَأَرۡسَلۡنَا عَلَيۡهِمۡ رِجۡزٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ بِمَا كَانُواْ يَظۡلِمُونَ ﴿١٦٢﴾

**161-162.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለነርሱም በዚች ከተማ ተቀመጡ። ከርሷም በፈለጋችሁት ስፍራ ብሉ። (የምንፈልገው) የኃጢ.ታችንን መርገፍ ብቻ ነው በሉም። የከተማይቱን በር አጎንብሳችሁ ግቡ ኃጢአቶቻችሁን ለእናንተ እንምራለንና። በጎ ለሠሩት ሰዎች በእርግጥ እንጨምራለን። በተባሉ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ከእነርሱም ውስጥ እነዚያ ራሳቸውን የበደሉ ሰዎች ከዚያ ለእነርሱ ከተባለው ሌላ የሆነን ቃል ለወጡ። በእነርሱም ላይ ይበድሉ በነበሩት በደል ምክንያት መአትን ከሰማይ ላክንባቸው።

وَسۡـَٔلۡهُمۡ عَنِ ٱلۡقَرۡيَةِ ٱلَّتِي كَانَتۡ حَاضِرَةَ ٱلۡبَحۡرِ إِذۡ يَعۡدُونَ فِي ٱلسَّبۡتِ إِذۡ تَأۡتِيهِمۡ حِيتَانُهُمۡ
يَوۡمَ سَبۡتِهِمۡ شُرَّعٗا وَيَوۡمَ لَا يَسۡبِتُونَ لَا تَأۡتِيهِمۡۚ كَذَٰلِكَ نَبۡلُوهُم بِمَا كَانُواْ يَفۡسُقُونَ ﴿١٦٣﴾

**163.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዚያች በባህሩ ዳርቻ ከነበረችው ከተማ በቅዳሜ ቀን ወሰን ባለፉ ጊዜ በሰንበታቸው ቀን አሳዎቻቸው

የተከማቹ ሆነው በሚመጡላቸው ጊዜ (የሆነውን) ጠይቃቸው። ሰንበትንም በማያከብሩበት (በሌላው) ቀን አይመጡላቸውም። እንደዚሁ በአመፃቸው ምክንያት እንሞክራቸዋለን።

وَإِذۡ قَالَتۡ أُمَّةٞ مِّنۡهُمۡ لِمَ تَعِظُونَ قَوۡمًا ٱللَّهُ مُهۡلِكُهُمۡ أَوۡ مُعَذِّبُهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدٗاۖ قَالُواْ مَعۡذِرَةً
إِلَىٰ رَبِّكُمۡ وَلَعَلَّهُمۡ يَتَّقُونَ ﴿١٦٤﴾ فَلَمَّا نَسُواْ مَا ذُكِّرُواْ بِهِۦٓ أَنجَيۡنَا ٱلَّذِينَ يَنۡهَوۡنَ عَنِ ٱلسُّوٓءِ
وَأَخَذۡنَا ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ بِعَذَابِۭ بَـِٔيسِۭ بِمَا كَانُواْ يَفۡسُقُونَ ﴿١٦٥﴾ فَلَمَّا عَتَوۡاْ عَن مَّا نُهُواْ عَنۡهُ
قُلۡنَا لَهُمۡ كُونُواْ قِرَدَةً خَٰسِـِٔينَ ﴿١٦٦﴾

**164-166.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱም ከፊሎቹ ህዝቦች አላህ አጥፊያቸው ወይም በብርቱ ቅጣት ቀጪቸው የሆኑትን ህዝቦች ለምን ትገስጻላችሁ? ባሉ ጊዜ ገሳጮቹ በጌታችሁ ዘንድ በቂ ምክንያት እንዲሆነንና እነርሱም ቢከለከሉ ብለን ነው ባሉበት ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። በእርሱም የተገሰፁበትን ነገር በተው ጊዜ እነዚያን ከክፉ የሚከለክሉትን ክፍሎች አዳንን። እነዚያንም የበደሉትን ሰዎች ያምፁ በነበሩበት ምክንያት በብርቱ ቅጣት ቀጣናቸው። ከእርሱም ከተከለከሉት ነገር በኮሩ ጊዜ ለእነርሱ ወራዶች ዝንጀሮች ሁኑ አልን (ሆኑም)።

وَإِذۡ تَأَذَّنَ رَبُّكَ لَيَبۡعَثَنَّ عَلَيۡهِمۡ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ مَن يَسُومُهُمۡ سُوٓءَ ٱلۡعَذَابِۗ إِنَّ رَبَّكَ
لَسَرِيعُ ٱلۡعِقَابِ وَإِنَّهُۥ لَغَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿١٦٧﴾

**167.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም እስከ ትንሳኤ ቀን ክፉ ቅጣትን የሚያቀምሳቸውን ወገን በነሱ ላይ በእርግጥ የሚልክ መሆኑን ባስታወቀ ጊዜ የሆነውን (አስታውሳቸው) ጌታህ በእርግጥ ቅጣቱ ፈጣን ነው እርሱም በእርግጥ እጅግ መሀሪና አዛኝ ነውና።

وَقَطَّعۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ أُمَمٗاۖ مِّنۡهُمُ ٱلصَّٰلِحُونَ وَمِنۡهُمۡ دُونَ ذَٰلِكَۖ وَبَلَوۡنَٰهُم بِٱلۡحَسَنَٰتِ
وَٱلسَّيِّـَٔاتِ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ﴿١٦٨﴾ فَخَلَفَ مِنۢ بَعۡدِهِمۡ خَلۡفٞ وَرِثُواْ ٱلۡكِتَٰبَ يَأۡخُذُونَ عَرَضَ
هَٰذَا ٱلۡأَدۡنَىٰ وَيَقُولُونَ سَيُغۡفَرُ لَنَا وَإِن يَأۡتِهِمۡ عَرَضٞ مِّثۡلُهُۥ يَأۡخُذُوهُۚ أَلَمۡ يُؤۡخَذۡ عَلَيۡهِم
مِّيثَٰقُ ٱلۡكِتَٰبِ أَن لَّا يَقُولُواْ عَلَى ٱللَّهِ إِلَّا ٱلۡحَقَّ وَدَرَسُواْ مَا فِيهِۗ وَٱلدَّارُ ٱلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ لِّلَّذِينَ
يَتَّقُونَۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴿١٦٩﴾

**168-169.** የኢስራኤልን ልጆችን በምድር ላይ የተለያዩ ህዝቦች አድርገንም ከፋፈልናቸው። ከእነርሱ መልካሞች አሉ። ከእነርሱም ከዚያ ሌላ የሆኑ አሉ። ይመለሱ ዘንድም በተድላዎችና በመከራወችም ሞከርናቸው። ከኋላቸውም መጽሐፉን የወረሱ መጥፎ ምትኮች በእነርሱ ቦታ ተተኩ። የዚህም የቅርቡን ጠፊ ጥቅም ይይዛሉ። ብጤውም ጥቅም ቢመጣላቸው የሚይዙት ሲሆኑ በሠራነው ለእኛ ምህረት ይደረግልናል ይላሉ። በአላህ ላይ በእውነት በቀር እንዳይናገሩ በእነርሱ ላይ የመጽሐፉ ቃል ኪዳን አልተያዘባቸውምን? በእርሱ ውስጥ ያለውንም አላነበቡምን? የመጨረሻይቱን አገር ለእነዚያ ጌታቸውን ለሚፈሩት ሰዎች ሁሉ በላጭ ናት። ይህን አታውቁምን?

وَٱلَّذِينَ يُمَسِّكُونَ بِٱلۡكِتَٰبِ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ إِنَّا لَا نُضِيعُ أَجۡرَ ٱلۡمُصۡلِحِينَ ﴿١٧٠﴾

**170.** እነዚያም መጽሐፉን ጠብቀው የሚይዙ፤ ሶላትንም በደንቡ የሰገዱ ሁሉ ምንዳቸውን እንከፍላቸዋለን። እኛ የመልካም ሠሪዎችን ምንዳ አናጠፋምና።

**ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (156-170) ከሚገኙ አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ወንጀልን አምኖ ከኃጢአቶች መመለስና ተውበት ማድረግ ጊዜ ሊሰጠው የማይገባ ግዴታ መሆኑን፤
2. የሰውን ልጅ ማቅናትም ሆነ ማጥመም የሚችለው አላህ ብቻ መሆኑን፤
3. ነብዩን (ﷺ) ማክበርና የርሳቸውን ፈለግ መከተል በሙስሊሞች ላይ ግዴታ መሆኑን፤
4. የነብዩ (ﷺ) መልዕክትና ጥሪ ለመላው የሰው ዘር በሙሉ እንደሆነ፤
5. የግለሰብና የህዝቦች መመራት የሚያረጋግጠው የነብዩን (ﷺ) ፈለግ መከተላቸው በተጨባጭ ሲረጋገጥ ስለ መሆኑን፤
6. ቁርአን ፍትህ የሚያስተምር፤ ፍትሃዊነትን የሚያሰፍን አድሎን የሚያወግዝ የአላህ መፅሀፍ ስለመሆኑ፤
7. አላህ ለህዝቦች የዋለውን ውለታና የሰጠውን ፀጋ አምነው ሰዎች ምስጋናን ለእርሱ ካላቀረቡ ማንም ይሁን ማን አላህ ደግሞ ጸጋውን ከላያቸው ላይ ለመግፈፍ ወደኋላ የማይል ጌታ መሆኑን፤
8. ማንኛውም የአላህን ጸጋ አጣጥሞ ምስጋናን ካላስከተለ የመጀመሪያውን ሊያልፍ ቢችልም ዳግም ለማመስገን ዝግጁ ካልሆነ ቅጣቱ እንደሚጠብቀው፤
9. በደግ ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል ኢስላማዊ ማህበረሰብን የመፍጠር ብቃት ያለው እጅግ ጠቃሚ ኢስላማዊ ሕግ መሆኑን፤
10. ስለ ታሪክ ተጨባጭ እውነታን የሚያስተምር ቁርአናዊ አንቀፅ መኖሩን፤
11. ከ መካከል ጥቂት መልካም ሰዎች እንደሚገኙ፤
12. አኼራን በመተው ዱንያን ብቻ ማሳደድ አስቀያሚ ድጊርት መሆኑንና የመጨረሻው ዓለም ከዱንያ የበለጠች ዘለዓለማዊ መኖሪያ መሆኗን፤
13. ቁርአንን በመማርና በማስተማር እንዲሁም ሕጉን ተግባራዊ በማድረግ በኩል ግፊትና አስተዋፅኦ ማድረግ ግዴታ መሆኑን እንማራለን።

۞ وَإِذْ نَتَقْنَا ٱلْجَبَلَ فَوْقَهُمْ كَأَنَّهُۥ ظُلَّةٌ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُۥ وَاقِعٌۢ بِهِمْ خُذُوا۟ مَآ ءَاتَيْنَٰكُم بِقُوَّةٍ
وَٱذْكُرُوا۟ مَا فِيهِ لَعَلَّكُمْ تَتَّقُونَ ﴿١٧١﴾

**171.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የጡርን ተራራ ነቅለን ከበላያቸው እንደ ጥላ ሆኖ ባነሳነውና እርሱም በእነርሱ ላይ ወዳቂ መሆኑን ባረጋገጡ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። የሰጠናችሁን በብርታት ያዙ። ትጠነቀቁም ዘንድ ውስጡ ያለውን ተገንዘቡ አልን።

وَإِذْ أَخَذَ رَبُّكَ مِنۢ بَنِىٓ ءَادَمَ مِن ظُهُورِهِمْ ذُرِّيَّتَهُمْ وَأَشْهَدَهُمْ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ أَلَسْتُ بِرَبِّكُمْ ۖ
قَالُوا۟ بَلَىٰ ۛ شَهِدْنَآ ۛ أَن تَقُولُوا۟ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ إِنَّا كُنَّا عَنْ هَٰذَا غَٰفِلِينَ ﴿١٧٢﴾ أَوْ تَقُولُوٓا۟ إِنَّمَآ
أَشْرَكَ ءَابَآؤُنَا مِن قَبْلُ وَكُنَّا ذُرِّيَّةً مِّنۢ بَعْدِهِمْ ۖ أَفَتُهْلِكُنَا بِمَا فَعَلَ ٱلْمُبْطِلُونَ ﴿١٧٣﴾ وَكَذَٰلِكَ
نُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ وَلَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ﴿١٧٤﴾

**172-174.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም ከአደም ልጆች ከጀርባቸው ዘሮቻቸውን ባወጣና ጌታችሁ አይደለሁምን? ሲል በነፍሶቻቸው ላይ ባስመሰከራቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ጌታችን ነህ መሰከርን አሉ በትንሳኤ ቀን ከዚህ ቃል ኪዳን ዘንጊዎች ነበርን እንዳትሉ። ወይም ጣኦታትን ያጋሩት ከኛ በፊት የነበሩት አባቶቻችን ብቻ ናቸው። እኛም ከእነርሱ በኋላ የሆንን ዘሮች ነበርን አጥፊዎቹ በሠሩት ጥፋት እኛን ታጠፋናለህን? እንዳትሉ (አስመሰከርናችሁ)። እንደዚሁም እንዲያስቡ እንዲመለሱም አንቀፆችን እናብራራለን።

وَٱتْلُ عَلَيْهِمْ نَبَأَ ٱلَّذِىٓ ءَاتَيْنَٰهُ ءَايَٰتِنَا فَٱنسَلَخَ مِنْهَا فَأَتْبَعَهُ ٱلشَّيْطَٰنُ فَكَانَ مِنَ
ٱلْغَاوِينَ ﴿١٧٥﴾ وَلَوْ شِئْنَا لَرَفَعْنَٰهُ بِهَا وَلَٰكِنَّهُۥٓ أَخْلَدَ إِلَى ٱلْأَرْضِ وَٱتَّبَعَ هَوَىٰهُ ۚ فَمَثَلُهُۥ
كَمَثَلِ ٱلْكَلْبِ إِن تَحْمِلْ عَلَيْهِ يَلْهَثْ أَوْ تَتْرُكْهُ يَلْهَث ۚ ذَّٰلِكَ مَثَلُ ٱلْقَوْمِ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟
بِـَٔايَٰتِنَا ۚ فَٱقْصُصِ ٱلْقَصَصَ لَعَلَّهُمْ يَتَفَكَّرُونَ ﴿١٧٦﴾

**175-176.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዚያን ተዐምራታችንን የሰጠነውንና ከዚያ ከእርሷ የወጣውን ሰይጣንም ያስከተለውን በዚህም ምክንያት ከጠማሞቹ የሆነውን ሰው ወሬ በእነርሱ ላይ አንብብላቸው። ብንፈልግ ኖሮ በርሷ ከፍ ባደረግነው ነበር። እርሱ ግን ወደ ምድር ተዘነበለ። ፍላጎቱንም ተከተለ። ብጤውም ብታባርረውም ምላሱን አውጥቶ እንደሚያለከልክ ወይም ብትተወው ምላሱን አውጥቶ የሚያለከልክ እንደሆነ

ውሻ ነው። ይህ የእነዚያ በአንቀፆቻችን ያስተባበሉት ህዝቦች ምሳሌ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያስተነትኑም ዘንድ ታሪኮችን ተርክላቸው።

ከሱረቱ አል አዕራፉ (175) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በልዑም ቢን ባዑራ የተባለን ሰው ታሪክ ለሙስሊሞች ለማስታወስ ነው። ይኸውም ይህ ግለሰብ ኢስመላህ አዕዘም የሚባለውን የአላህ ታላቅ ስም ያውቅ ስለነበር ሙሳ በአገራቸው ሲመጡ ዘመዶቹ እና የአጎቶቹ ልጆች ወደ እሱ በመምጣት «ሙሳ ብርቱ ሰው ነው ብዙም ሠራዊት አለው። ያሸነፈን እንደሆነ ያጠፉናል። ሙሳንና ሰራዊቱን እንዲመልስልን አላህን ለምንልን» በማለት ሲጠይቁት «አላህን ለምኜ ሙሳንና ሠራዊቱን ካስመለስኩ ዱንያዬም ሆነ አኼራዬ ይጠፉብኛል» አላቸው። እነሱም ችክ ብለው ሲጨቀጭቁት ለእነሱ ደስ ይበላቸው በሚል በሙሳና በሰራዊቱ ላይ ዱአ አደረገ። በዚህም የተነሳ አላህ ሰጥቶት የነበረውን ፀጋና ተቀባይነት ቀማው። ይህን ታሪክ ለማስታወስ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

سَآءَ مَثَلًا ٱلْقَوْمُ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا وَأَنفُسَهُمْ كَانُوا۟ يَظْلِمُونَ ﴿١٧٧﴾ مَن يَهْدِ ٱللَّهُ فَهُوَ
ٱلْمُهْتَدِى ۖ وَمَن يُضْلِلْ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿١٧٨﴾

**177-178.** የእነዚያ በአንቀፆቻችን ያስተባበሉትና ነፍሶቻቸውን ይበድሉ የነበሩት ሰዎች ምሳሌ ከፋ። አላህ የሚያቀናው ሰው ሁሉ ቅን ማለት እርሱ ብቻ ነው። የሚያጠማቸውም ሰዎች እነዚያ ከሳሪዎቹ ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው።

**ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (171-178) ከሚገኙ አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የውስጠ ሚስጢራዊ ማንነት፤
2. ከሃዲ ዛሬ በምድር ላይና ጥንት ደግሞ ነፍስያው በአለመ ዘራህ ሁለት ጊዜ አላህን የካደ በመሆኑ የሚገባውም ቅጣት እንዲሁ እጥፍ ድርብ እንደሚሆን፤ የሙእሚን ነፍስም ዛሬም ሆነ ትላንት በተደጋጋሚ አማኝነቷን ስላረጋገጠች እጥፍ ድርብ ምንዳ እንደሚሰጣት፤
3. ሕግጋቱንም ያለመጠበቅና ያለማክበር ቁርአንን ማንበብ የሰውን ልጅ የመጨረሻ አደጋ ላይ የሚጨምር አደገኛ ተግባር መሆኑን፡
4. መመራት የሚገኘው ከአላህ ብቻ በመሆኑ አዘውትሮ እርሱን መለመን እንደሚገባ እንማራለን።

وَلَقَدْ ذَرَأْنَا لِجَهَنَّمَ كَثِيرًا مِّنَ ٱلْجِنِّ وَٱلْإِنسِ ۖ لَهُمْ قُلُوبٌ لَّا يَفْقَهُونَ بِهَا وَلَهُمْ
أَعْيُنٌ لَّا يُبْصِرُونَ بِهَا وَلَهُمْ ءَاذَانٌ لَّا يَسْمَعُونَ بِهَآ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ كَٱلْأَنْعَٰمِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ ۚ
أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْغَٰفِلُونَ ﴿١٧٩﴾

**179.** ከአጋንንትም ሆነ ከሰዎች መካከል ብዙዎችን ለገሀነም በእርግጥ ፈጠርን። ለእነርሱ በርሳቸው የማያውቁባቸው ልቦች አሏቸው። ለእነርሱም በርሳቸው የማያዩባቸው ዓይኖች አሏቸው። በርሳቸው ለእነርሱም የማይሰሙባቸው ጆሮዎች አሏቸው። እነዚያ እንደ እንስሳዎች ናቸው። ይልቁንም እነርሱ በጣም የተሳሳቱ ህዝቦ ናቸው። እነዚያ ዘንጊዎቹ እነርሱ ብቻ ናቸው።

وَلِلَّهِ ٱلْأَسْمَآءُ ٱلْحُسْنَىٰ فَٱدْعُوهُ بِهَا ۖ وَذَرُوا۟ ٱلَّذِينَ يُلْحِدُونَ فِىٓ أَسْمَٰٓئِهِۦ ۚ
سَيُجْزَوْنَ مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿١٨٠﴾

**180.** ለአላህም መልካም ስሞች አሉት። እናም በዱዓ ጊዜ በእነርሱ ብቻ ጥሩት። እነዚያን ስሞቹን የሚያጣምሙትን ክፍሎች ተዋቸው። ይሠሩት የነበሩትን ነገር በእርግጥ ይመነዳሉ።

وَمِمَّنْ خَلَقْنَآ أُمَّةٌ يَهْدُونَ بِٱلْحَقِّ وَبِهِۦ يَعْدِلُونَ ﴿١٨١﴾

**181.** ከፈጠርናቸውም ሰዎች መካከል በእውነት የሚመሩና በእውነት ፍርድን የሚያስተካክሉ ህዝቦች አሉ።*

* በዚህ አንቀፅ እንደዚህ የተባሉት ህዝቦች የነብዩ ኡመቶች መሆናቸውን የሚያመላክቱ ብዙ መረጃዎች አሉ። ቀታዳ የሚባሉ ዓሊም ነብዩ ይህን አንቀፅ ባነበቡ ጊዜ «ይህ ለእናንተ የተሰጠ ነው። ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችም ተመሳሳዩ ተሰጥቷቸው ነበር» እንዳሉ ዘግበዋል። ረቢዕ ኢብኑ አነስ ነብዩ ይህን አንቀፅ አንብበው «ከህዝቦቼ መካከል ሀቅን ይዘው የሚጓዙ አሉ። ነብዩ ዒሳ እስከሚመጡ ድረስ» ብለዋል። አንዳንድ ዐሊሞች ይህንን የቁርኣን አንቀፅ መረጃ በማድረግ (በየጊዜው ያሉ ኡለማዎች በአንድ ነገር መሰባሰብ (እጅማእ) ማስረጃ ነው። እስከ ዓለም ፍፃሜ ድረስም ሙጅተሂዶች እንደማይጠፉ ያስረዳል ይላሉ።

وَٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا سَنَسْتَدْرِجُهُم مِّنْ حَيْثُ لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٨٢﴾ وَأُمْلِى لَهُمْ ۚ إِنَّ كَيْدِى مَتِينٌ ﴿١٨٣﴾

**182-183.** እነዚያን በአንቀፆቻችን ያስተባበሉትን ሰዎች ከማያውቁት ስፍራ ቀስ በቀስ ምቾትን በመጨመር እናዘናጋቸዋለን። ለእነርሱም ጊዜ እሰጣቸዋለሁ። ቅጣቴ ብርቱ ነውና።

أَوَلَمْ يَتَفَكَّرُوا۟ ۗ مَا بِصَاحِبِهِم مِّن جِنَّةٍ ۚ إِنْ هُوَ إِلَّا نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿١٨٤﴾ أَوَلَمْ يَنظُرُوا۟ فِى مَلَكُوتِ
ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَمَا خَلَقَ ٱللَّهُ مِن شَىْءٍ وَأَنْ عَسَىٰٓ أَن يَكُونَ قَدِ ٱقْتَرَبَ أَجَلُهُمْ ۖ فَبِأَىِّ
حَدِيثٍۭ بَعْدَهُۥ يُؤْمِنُونَ ﴿١٨٥﴾ مَن يُضْلِلِ ٱللَّهُ فَلَا هَادِىَ لَهُۥ ۚ وَيَذَرُهُمْ فِى طُغْيَٰنِهِمْ يَعْمَهُونَ ﴿١٨٦﴾

**184-186.** በነብያቸው (በሙሐመድ) ምንም እብደት የሌለበት መሆኑን አያስተውሉምን? እርሱ ግልጽ አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለም። በሰማያትና በምድር ግዛት ውስጥ ከማንኛውም ነገር አላህ በፈጠራቸው ሁሉ የሞት ጊዜያቸውም በእርግጥ መቅረቡ የሚፈራ መሆኑን አያስተውሉምን? ለመሆኑ እነርሱ ከቁርኣን ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ። አላህ የሚያጠመው ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም። በጥመታቸውም ውስጥ የሚዋልሉ ሲሆኑ ይተዋቸዋል።

يَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلسَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَىٰهَا ۖ قُلْ إِنَّمَا عِلْمُهَا عِندَ رَبِّى ۖ لَا يُجَلِّيهَا لِوَقْتِهَآ إِلَّا هُوَ ۚ
ثَقُلَتْ فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ لَا تَأْتِيكُمْ إِلَّا بَغْتَةً ۗ يَسْـَٔلُونَكَ كَأَنَّكَ حَفِىٌّ عَنْهَا ۖ قُلْ إِنَّمَا
عِلْمُهَا عِندَ ٱللَّهِ وَلَـٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٨٧﴾ قُل لَّآ أَمْلِكُ لِنَفْسِى نَفْعًا
وَلَا ضَرًّا إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُ ۚ وَلَوْ كُنتُ أَعْلَمُ ٱلْغَيْبَ لَٱسْتَكْثَرْتُ مِنَ ٱلْخَيْرِ وَمَا مَسَّنِىَ ٱلسُّوٓءُ ۚ
إِنْ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٌ وَبَشِيرٌ لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿١٨٨﴾

**187-188.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ትንሳኤ መቼ እንደምትመጣ ይጠይቁሃል። እውቀቷ በጌታዬ ዘንድ ብቻ ነው። በመከሰቻዋ ጊዜም እርሱ እንጂ ሌላ አይገልፅላችሁም። በሰማያትና በምድርም ከበደች። በድንገት ቢሆን እንጂ አትመጣባችሁም በላቸው። ስለ እርሷ በደንብ እንደተረዳህ አድርገው ይጠይቁሃል። እውቀቷ ግን አላህ ዘንድ ብቻ ነው።* ግን አብዛኞቹ ሰዎች ይህን ነገር ጠንቅቀው አያውቁም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የፈለገዉን በስተቀር ለራሴ ጥቅምንም ሆነ ጉዳት ማምጣት አልችልም። የሩቅን ሚስጥር የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ሁሉ ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር። እኔ ለሚያምኑ ህዝቦች አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው።

* ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) «አላህ ለግፈኛ ጊዜ ይሰጠዋል። የያዘው ጊዜ ግን አያመልጠውም» ብለዋል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ እንዳስላተላፉት እንዲህም ብለዋል።«የስውር ነገሮች መክፈቻ ቁልፎች አምስት ናቸው። እነርሱም «አላህ የሰዓቲቱ እውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው። ዝናቡንም ያወርዳል፤ በማሕፀኖችም ውስጥ ያለን ሁሉ ያውቃል፤ ማንኛይቱም ነፍስም በየትኛው ምድር እንደምትሞት አንተ አታውቅም አላህ ውስጠ ዐዋቂ ነው» (ሉቅማን፡ 34)

۞ هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن نَّفْسٍ وَٰحِدَةٍ وَجَعَلَ مِنْهَا زَوْجَهَا لِيَسْكُنَ إِلَيْهَا ۖ فَلَمَّا تَغَشَّىٰهَا
حَمَلَتْ حَمْلًا خَفِيفًا فَمَرَّتْ بِهِۦ ۖ فَلَمَّآ أَثْقَلَت دَّعَوَا ٱللَّهَ رَبَّهُمَا لَئِنْ ءَاتَيْتَنَا صَـٰلِحًا
لَّنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّـٰكِرِينَ ﴿١٨٩﴾ فَلَمَّآ ءَاتَىٰهُمَا صَـٰلِحًا جَعَلَا لَهُۥ شُرَكَآءَ فِيمَآ ءَاتَىٰهُمَا ۚ فَتَعَـٰلَى
ٱللَّهُ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿١٩٠﴾

**189-190.** (ሰዎች ሆይ)፣ እርሱ ያ፣ ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁና ከእርሷም መቀናጆዋን ወደ እርሷ ይረካ ዘንድ የፈጠረ ነው። በተገናኛትም ጊዜ ቀላልን እርግዝና አረገዘች። ጽንሱን ይዛው ሄደች። ባረገዘችም ጊዜ ደግን ልጅ ብትሰጠን በእርግጥ ከአመስጋኞቹ እንሆናለን ሲሉ ጌታቸውን አላህን ለመኑ።

መልካምን ልጅ በሰጣቸውም ጊዜ በሰጣቸው ልጅ ስም ለእርሱ ተጋሪዎችን አደረጉለት። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ላቀ።

أَيُشۡرِكُونَ مَا لَا يَخۡلُقُ شَيۡـٔٗا وَهُمۡ يُخۡلَقُونَ ١٩١ وَلَا يَسۡتَطِيعُونَ لَهُمۡ نَصۡرٗا وَلَآ أَنفُسَهُمۡ
يَنصُرُونَ ١٩٢ وَإِن تَدۡعُوهُمۡ إِلَى ٱلۡهُدَىٰ لَا يَتَّبِعُوكُمۡۚ سَوَآءٌ عَلَيۡكُمۡ أَدَعَوۡتُمُوهُمۡ أَمۡ أَنتُمۡ
صَٰمِتُونَ ١٩٣ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ عِبَادٌ أَمۡثَالُكُمۡۖ فَٱدۡعُوهُمۡ فَلۡيَسۡتَجِيبُواْ
لَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٩٤

**191-194.** ምንንም የማይፈጥሩትንና እነርሱ ራሳቸው የሚፈጥሯቸውን ፍጡሮች በአላህ ያጋራሉን? ለነርሱም መርዳትን የማይችሉትን ነፍሶቻቸውንም እንኳን የማይረዱትን ያጋራሉን? (ከሀዲያን ሆይ)፣ ጣኦቶቹን ወደ ቅን መንገድ ብትጠሯቸውም አይከተሏችሁም። ብትጠሯቸው ወይም ዝምተኞች ብትሆኑም በእናንተ ላይ እኩል ነው። (ከሀዲያን ሆይ)፣ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣኦቶች ብጤዎቻችሁ እና እራሳቸው አላህን ተገዢዎች ናቸው። እውነተኞች ከሆናችሁ እስቲ ጥሯቸውና ለእናንተ ይመልሱላችሁ።

أَلَهُمۡ أَرۡجُلٞ يَمۡشُونَ بِهَآۖ أَمۡ لَهُمۡ أَيۡدٖ يَبۡطِشُونَ بِهَآۖ أَمۡ لَهُمۡ أَعۡيُنٞ يُبۡصِرُونَ بِهَآۖ
أَمۡ لَهُمۡ ءَاذَانٞ يَسۡمَعُونَ بِهَاۗ قُلِ ٱدۡعُواْ شُرَكَآءَكُمۡ ثُمَّ كِيدُونِ فَلَا تُنظِرُونِ ١٩٥
إِنَّ وَلِـِّۧيَ ٱللَّهُ ٱلَّذِي نَزَّلَ ٱلۡكِتَٰبَۖ وَهُوَ يَتَوَلَّى ٱلصَّٰلِحِينَ ١٩٦ وَٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ
لَا يَسۡتَطِيعُونَ نَصۡرَكُمۡ وَلَآ أَنفُسَهُمۡ يَنصُرُونَ ١٩٧

**195-197.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነርሱ በእርሳቸው የሚሄዱባቸው እግሮች አሉዋቸውን? ወይስ ለነርሱ በእርሳቸው የሚጨብጡባቸው እጆች አሏቸውን? ወይስ ለነሱ በርሳቸው የሚያዩባቸው አይኖች አሏቸውን? ወይስ ለነርሱ የሚሰሙባቸው ጆሮዎች አሏቸውን? ያጋራችኋቸውን ጥሩና ከዚያ አሲሩብኝ። ጊዜም አትስጡኝ ፈፅሞ አልፈራችሁም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የእኔ ረዳቴ ያ ቁርኣንን ያወረደልኝ አላህ ነው። እርሱ መልካም ሠሪዎችን ሁሉ ይረዳልና በላቸው። (አጋሪዎች ሆይ)፣ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣኦታት ሁሉ ሊረዷችሁ አይችሉም። ነፍሶቻቸውንም እንኳን አይረዱም።

وَإِن تَدۡعُوهُمۡ إِلَى ٱلۡهُدَىٰ لَا يَسۡمَعُواْۖ وَتَرَىٰهُمۡ يَنظُرُونَ إِلَيۡكَ وَهُمۡ لَا يُبۡصِرُونَ ١٩٨
خُذِ ٱلۡعَفۡوَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡعُرۡفِ وَأَعۡرِضۡ عَنِ ٱلۡجَٰهِلِينَ ١٩٩ وَإِمَّا يَنزَغَنَّكَ مِنَ ٱلشَّيۡطَٰنِ
نَزۡغٞ فَٱسۡتَعِذۡ بِٱللَّهِۚ إِنَّهُۥ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ٢٠٠

**198-200.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ ቀናው መንገድ እንዲመሩ ብትጠሯቸው አይሰሙም። እነርሱንም የማያዩ ሲሆኑ ወደ አንተ ሲመለከቱ ታያቸዋለህ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፤ ይቅርባይነትን ያዝ። በመልካምም እዘዝ። ባለጌዎቹንም ተዋቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሰይጣን ተንኮል ጉትጎታ ቢያጋጥምህ በአላህ ብቻ ተጠበቅ። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነውና።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوۡاْ إِذَا مَسَّهُمۡ طَٰٓئِفٞ مِّنَ ٱلشَّيۡطَٰنِ تَذَكَّرُواْ فَإِذَا هُم مُّبۡصِرُونَ ٢٠١
وَإِخۡوَٰنُهُمۡ يَمُدُّونَهُمۡ فِي ٱلۡغَيِّ ثُمَّ لَا يُقۡصِرُونَ ٢٠٢

**201-202.** እነዚያ አላህን የሚፈሩ ሰዎች የሰይጣን ልክፍት ባጋጠማቸው ጊዜ ጌታቸውን ያስታውሳሉ። ወዲያውም እነርሱ ጥፋታቸውን ተመልካቾች ይሆናሉ። ወንድሞቻቸውም ጥመትን ይጨምሩላቸዋል። ከዚያ እነርሱ አይገቱም።

وَإِذَا لَمۡ تَأۡتِهِم بِـَٔايَةٖ قَالُواْ لَوۡلَا ٱجۡتَبَيۡتَهَاۚ قُلۡ إِنَّمَآ أَتَّبِعُ مَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّ مِن رَّبِّيۚ هَٰذَا بَصَآئِرُ
مِن رَّبِّكُمۡ وَهُدٗى وَرَحۡمَةٞ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ٢٠٣

**203.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተዐምርም ባላመጣህላቸው ጊዜ በራስህ ለምን አትመርጣትም ይላሉ*። ከጌታዬ ወደ እኔ የተወረደውን ብቻ እከተላለሁ። ይህ ቁርአን ከጌታችሁ የተወረደ ሲሆን ለሚያምኑ ህዝቦች ሁሉ መረጃዎችና፤ መመሪያ እዝነት ነው በላቸው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ «የመካ ሕዝቦች የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተዓምራትን ያሳዩዋቸው ዘንድ ጠየቋቸው። እሳቸውም የጨረቃን መሰንጠቅ አሳዩዋቸው» ብለዋል።

وَإِذَا قُرِئَ ٱلۡقُرۡءَانُ فَٱسۡتَمِعُواْ لَهُۥ وَأَنصِتُواْ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ٢٠٤ وَٱذۡكُر رَّبَّكَ فِي نَفۡسِكَ
تَضَرُّعٗا وَخِيفَةٗ وَدُونَ ٱلۡجَهۡرِ مِنَ ٱلۡقَوۡلِ بِٱلۡغُدُوِّ وَٱلۡأٓصَالِ وَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡغَٰفِلِينَ ٢٠٥
إِنَّ ٱلَّذِينَ عِندَ رَبِّكَ لَا يَسۡتَكۡبِرُونَ عَنۡ عِبَادَتِهِۦ وَيُسَبِّحُونَهُۥ وَلَهُۥ يَسۡجُدُونَ۩ ٢٠٦

**204-206.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ቁርኣን በሚነበብበት ጊዜ እርሱን በጥሞና አድምጡ። ፀጥም በሉ ይታዘንላችኋልና (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህን በሚስጥር ተናንሰህና ፈርተህ ከጩኸት በታች በሆነ ድምፅ በጥዋትና በማታ አውሳው። ከዘንጊዎቹም አትሁን። እነዚያ በጌታህ ዘንድ ያሉት መላዕክት እንኳን እርሱን ከመገዛት ፈፅሞ አይኮሩም። ሁልጊዜም ያወድሱታል። ለእርሱም ብቻ ይሰግዳሉ።

**ከሱረቱ አል አዕራፍ ከአንቀፅ (187-206) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦችዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሰዎች ፈጣሪያቸውን ከካዱ በክህደታቸው ምክንያት ከእንስሳት በታች እንደሚሆኑ፤
2. አላህ የመልካም ስሞች ባለቤት የሆነ ጌታ በመሆኑ መልካም ስሞቹ እያወሱ እርሱን መለመን ያለውን ጠቀሜታና ተገቢነት፤
3. የአላህን መልካም ስሞች መግለጫ የሆኑ ቃላትን መቀየር ትርጉማቸውን መለወጥ ከፍተኛ ወንጀል ስለመሆኑ፤
4. ቁርኣንን ማስተባበል ሕግጋቱንም ያለመቀበል ያለውን የከፋ ቅጣትና መቼም ቢሆን ተስፋ የማይጣልበት ስለ መሆኑ፤
5. ሰው እድሜው ስንት እንደሆነና መች ይህችን ዓለም እንደሚሰናበት አለማወቁን በየእለቱ በማስታወስ ደካማነቱን ማመን እንደሚገባው፤
6. በቁርኣን ያልተመከረ ሰው ምንም ኃይል ሊያስተካክለውና ሊመክረው የማይችል ስለ መሆኑ፤
7. ስለ ቂያማ ቀን ቁርጠኛ ቀጠሮና መች እንደሆነ ከአላህ ውጭ ማንም የማያውቅ ስለመሆኑ፤
8. ነብዩ (ﷺ) የአላህ መልዕክተኛ ከመሆናቸው ጋር በራሳቸው ላይ ጉዳትንም ሆነ ጥቅም የማድረስ ኃይል የሌላቸው እና ለሌላውም ሰው እንደዚሁ ጥቅም ሊቸሩት ጉዳትን ሊያነሱለት የማይችሉ በመሆኑ እርሳቸውን መለመን የተከለከለ መሆኑን፤
9. ሌላው ከአናቅፅ ከምናገኘው ነጥብ ሙሽሪኮች የሚገዙት ጣኦት የማይሰማ፤ የማያይ፤ የማይጠቅም መሆኑን ቁርኣን እንዳጋለጠ፤ እንዲሁም ሰይጣን እናታችን ሐዋን በማሳሳት እንዴት አድርጎ የአላህን ትዕዛዛት እንዳስጣሳቸው፤
10. የሰው ዘር መነሻና የሰዎች በሙሉ አባትና እናት አደምና ሐዋ መሆናቸውን፤
11. ኢብሊስ እናታችንን ሐዋ በመወስወስ እንዴት አድርጎ የአላህን ትዕዛዝ እንዳስጣላቸው፤
12. መልካም ስነ. ምግባሮችን መከተል ኢስላማዊ ግዴታ ነው። ሰይጣን ሊያታልለን የተንኮል መረቡን ሲዘረጋ በአላህ መጠበቅ ያስፈልጋል። በአላህ ላይ በመመካት ውሸትን ያለምንም ፍርሀት ማጋለጥ፤ መዋጋት ከሙስሊሞች ይጠበቃል። እንዲሁም የሽርክንና የወንጀልን መጥፎነት በማጋለጥ ዝርዝር መረጃና ትምህርት መስጠት ተወዳጅ ኢስላማዊ ተግባር ነው።
13. መልካም ሥነ. ምግባሮች መከተል ከኢስላማዊ ግዴታዎች የሚካተት መሆኑን፤
14. ነብዩ (ﷺ) ከተሰጣቸው ተአምራት በሙሉ ዘመን የማይሽረው ቁርኣን ትልቁን ስፍራ እንደሚይዝ፤
15. ቁርኣንን ሲነበብ በጥሞና ማዳመጥ ያለውን ግዴታነት፤
16. ጠዋትና ማታ አላህን ማስታወስ፤ ውለታዎቹንና ፀጋዎች መዘከር፤ እርሱን ማወደስ ግዴታ ስለመሆኑ፤
17. አላህን በማስታወሱ ሂደት በሚስጥር መሆኑ ተመራጭና ለአላህ መተናነስ እንዲሁም የልብ ፍራቻ መሰነቅ ግዴታ መሆኑን እንረዳለን።

በአላህ ፈቃድ የአል -አዕራፍ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (8)
# በጦርነት የተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል አንፋል)

سُورَةُ الأَنفَالِ

**የወረደው በመዲና ነው። የአናቅፁ ብዛት (75) ናቸው።**

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَسۡـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلۡأَنفَالِۖ قُلِ ٱلۡأَنفَالُ لِلَّهِ وَٱلرَّسُولِۖ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَصۡلِحُواْ ذَاتَ بَيۡنِكُمۡۖ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ
وَرَسُولَهُۥٓ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ١ إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتۡ قُلُوبُهُمۡ وَإِذَا تُلِيَتۡ
عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُهُۥ زَادَتۡهُمۡ إِيمَٰنٗا وَعَلَىٰ رَبِّهِمۡ يَتَوَكَّلُونَ ٢ ٱلَّذِينَ يُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَمِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ
يُنفِقُونَ ٣ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ حَقّٗاۚ لَّهُمۡ دَرَجَٰتٌ عِندَ رَبِّهِمۡ وَمَغۡفِرَةٞ وَرِزۡقٞ كَرِيمٞ ٤

**1-4.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ይጠይቁሃል። በጦርነት የተማረኩ ገንዘቦች የአላህና የመልእክተኛው ናቸው። ስለዚህ አላህን ፍሩ። በመካከላችሁ ያለውንም ሁኔታ አሳምሩ። ትክክለኛ አማኞች ከኾናችሁ አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ በላቸው። ፍፁም አማኞች ማለት እነዚያ አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚፈሩ፤ በእነርሱም ላይ የቁርኣን አንቀፆች በተነበቡ ጊዜ እምነትን የሚጨምሩላቸውና በሁሉ ነገር በጌታቸው ላይ ብቻ የሚመኩ ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚያ ሰላትን (ወቅቱን ጠብቀውና ደንቡን አሟልተው) የሚሰግዱና ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱ ናቸው። እነዚያ በእውነት አማኞች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። ለእነርሱ በጌታቸው ዘንድ ብዙ ደረጃዎች፤ የአላህ ምሕረትና የከበረ ሲሳይ አለላቸው።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ይህ ምዕራፍ በሙሉ የወረደው በበድር ዘመቻና በዘመቻ ላይ በተማረከው ንብረት ምክንያት ነው። የበድር ዘመቻ ዕለት ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) «ከጠላት ጦር አንድ ወታደር የገደለ የሟችን ልብስና ትጥቅ ይሸለማል። ምርኮ እያመጣም ከምርኮው የሚገኘው ቁሳቁስ በሙሉ ለማረከው ሰው ስጦታ ይበረከትለታል» በማለት ሲያውጁ ወጣቶቹ የሙስሊም ሠራዊቶች ሞራላቸው ተነሣሣና ወደ ጦርነቱ ዘልቀው በመግባት ጠላትን መግደልና መማረኩ ላይ ተረባረቡ። በእድሜ የገፉት ሽማግሌዎቹ የሠራዊቱ

አባላት ደግሞ ከሙስሊሙ ይልቅ ሠንደቅ ስር በመዋል የጦርነቱን ኋላ ክፍል ገትረው ያዙ። ከዚያም ጦርነቱ ሲያበቃ የምርኮ ክፍፍሉ ላይ ሽማግሌዎቹ ለወጣቶቹ የማረኩትን ንብረት እንዲያካፍሏቸው ሲጠይቋቸው ወጣቶቹ ደግሞ ምርኮው የእነርሱ ብቻ መሆኑን በመግለፅ አሻፈረኝ አሉ። እናም ወደ ነብዩ (ﷺ) ዘንድ ቀረቡ። ከዚያም አላህ የምርኮ ክፍፍል ምን መምሰል እንዳለበትና እንዴት እንደ ሚከፋፈሉ የእያንዳንዱን ሰው ድርሻ በዚህ አንቀፅ ወሰነ። (አቡ ዳዉድ፤ ሃኪም፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

كَمَآ أَخۡرَجَكَ رَبُّكَ مِنۢ بَيۡتِكَ بِٱلۡحَقِّ وَإِنَّ فَرِيقٗا مِّنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ لَكَٰرِهُونَ ٥ يُجَٰدِلُونَكَ
فِي ٱلۡحَقِّ بَعۡدَ مَا تَبَيَّنَ كَأَنَّمَا يُسَاقُونَ إِلَى ٱلۡمَوۡتِ وَهُمۡ يَنظُرُونَ ٦

**5-6.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ይህ በምርኮ ክፍያ ሂደት ላይ የታየው የከፊሉ ሰው መጥላት ምሳሌው) ከአማኞች ከፊሉ እየጠሉ ጌታህ ከቤትህ በእውነት ላይ እንዳወጣህ ምሳሌ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱ እያዩ ወደ ሞት እንደሚነዱ ኾነው በእውነቱ ነገር ላይ (በመጋደል ግዴታነት) ከተገለፀላቸው በኋላ ይከራከሩሃል።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (5) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በመዲና እያሉና «በአቡሱፍያን የሚመራው የንግድ ልዑክ እየመጣ ነው» ሲባሉ ለሙስሊሞቹ «ምን ይመስላችኋል? ምን አልባትም አላህ ይህችን የንግድ ቡድን በቁጥጥራችን ስር በማዋል ሊቸረን ይችላል» በማለት የተወሠኑ ሰዎችን ይዘው ወደ መንገዱ መጓዝ ጀመሩ። አንድ ቀን ወይም ሁለት ቀን ከሄዱ በኋላ የቡድኑን ማምለጥና መኮች ለጦርነት እየመጡ መሆኑን ሲሰሙ «ምን ይመስላችኋል» አሏቸው። «እነሱን ለመዋጋት አቅም የለንም። ወጥተን የነበረው ለንግዱ ማህበረሠብ ነበር» ሲሉ ሚቅዳድ ቢኑ አል. አስወድ የተባለው ሶሀባ ከመካከላቸው በመነሣት የሙሣ ሠዎች "ሂድ አንተና ጌታህ ተዋጉ እኛ እዚሁ ተቀማጮች ነን እንዳሉት አትበሉ" ብሎ መከራቸው። ሁላቸውም «እንደዚህማ አንልም» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَإِذۡ يَعِدُكُمُ ٱللَّهُ إِحۡدَى ٱلطَّآئِفَتَيۡنِ أَنَّهَا لَكُمۡ وَتَوَدُّونَ أَنَّ غَيۡرَ ذَاتِ ٱلشَّوۡكَةِ تَكُونُ
لَكُمۡ وَيُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُحِقَّ ٱلۡحَقَّ بِكَلِمَٰتِهِۦ وَيَقۡطَعَ دَابِرَ ٱلۡكَٰفِرِينَ ٧ لِيُحِقَّ ٱلۡحَقَّ
وَيُبۡطِلَ ٱلۡبَٰطِلَ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡمُجۡرِمُونَ ٨ إِذۡ تَسۡتَغِيثُونَ رَبَّكُمۡ فَٱسۡتَجَابَ لَكُمۡ أَنِّي
مُمِدُّكُم بِأَلۡفٖ مِّنَ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ مُرۡدِفِينَ ٩ وَمَا جَعَلَهُ ٱللَّهُ إِلَّا بُشۡرَىٰ وَلِتَطۡمَئِنَّ بِهِۦ
قُلُوبُكُمۡۚ وَمَا ٱلنَّصۡرُ إِلَّا مِنۡ عِندِ ٱللَّهِۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ١٠

**7-10.** (እናንተ ተከራካሪዎች ሆይ)፣ አላህ ከሁለቱ ጭፍሮች አንደኛዋን ለእናንተ ናት ሲል ተስፋ በሰጣችሁና የኃይል ባለቤት ያልኾነችውን የነጋዴይቱን ቡድን ለእናንተ ልትሆን በወደዳችሁ ጊዜ አላህን በተስፋ ቃላቱ እውነቱን ማረጋገጡን ሊገልጽና የካሓዲያንም መጨረሻ ሊቆርጥ በፈለገ ጊዜ (የሆነውን

አስታውስ)። ይህንንም ያደረገው አጋሪዎቹ ቢጠሉም እውነቱን ሊያረጋግጥና ክህደትን ሊያጠፋ ነው። (ሙስሊሞች ሆይ) ከጌታችሁ እርዳታን በፈለጋችሁ ጊዜ እኔ በሺ መላዕክት ተከታታዮች ሲሆኑ እረዳችኋለሁ ሲል ለእናንተ የተቀበላችሁን (አስታውሱ)። አላህ ይህንን እርዳታ ለብስራትና ልቦቻችሁ በእርሱ ሊረኩበት እንጂ ለሌላ አላደረገውም። ድልም የሚገኘው ከአላህ ዘንድ ብቻ ነው። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

إِذْ يُغَشِّيكُمُ ٱلنُّعَاسَ أَمَنَةً مِّنْهُ وَيُنَزِّلُ عَلَيْكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً لِّيُطَهِّرَكُم بِهِۦ وَيُذْهِبَ عَنكُمْ رِجْزَ ٱلشَّيْطَٰنِ وَلِيَرْبِطَ عَلَىٰ قُلُوبِكُمْ وَيُثَبِّتَ بِهِ ٱلْأَقْدَامَ ﴿١١﴾ إِذْ يُوحِى رَبُّكَ إِلَى ٱلْمَلَٰٓئِكَةِ أَنِّى مَعَكُمْ فَثَبِّتُوا۟ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ۚ سَأُلْقِى فِى قُلُوبِ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ٱلرُّعْبَ فَٱضْرِبُوا۟ فَوْقَ ٱلْأَعْنَاقِ وَٱضْرِبُوا۟ مِنْهُمْ كُلَّ بَنَانٍ ﴿١٢﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ شَآقُّوا۟ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ ۚ وَمَن يُشَاقِقِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَإِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿١٣﴾ ذَٰلِكُمْ فَذُوقُوهُ وَأَنَّ لِلْكَٰفِرِينَ عَذَابَ ٱلنَّارِ ﴿١٤﴾

**11-14.** (እናንተ ሙእሚኖች ሆይ!)፣ ከእርሱ በኾነው ፀጥታ (በጦር ግንባር) በእንቅልፍ በሸፈናችሁና ውሃንም በእርሱ ሊያጠራችሁ የሰይጣንንም ጉትጎታ ከናንተ ላይ ሊያስወግድላችሁ ልቦቻችሁንም (በትዕግሥት) ሊያጠነክርላችሁ በእርሱም ጫማዎችን (ባሸዋው) ላይ ሊያደላድልላችሁ በእናንተ ላይ ከሰማይ ዝናብን ባወረደ ጊዜ (የሆነውን አስታውሱ)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ወደ መላዕክቱ እኔ በእርዳታዬ ከናንተ ጋር ነኝና እነዚያን በእኔ ያመኑትን ሰዎች አፅናኑ። በእነዚያ በአላህ በካዱት ልቦች ውስጥ ደግሞ ፍርሀትን እጥላለሁ። ከአንገቶችም በላይ እራሶችን ምቱ። ከእነርሱም የቅርንጫፎችን አትቆች መለያ ሁሉ ምቱ ሲል ያወረደውን (አስታውስ)። ይህ የሆነው አላህንና መልዕክተኛው ስለተቃወሙ ነው። አላህንና መልዕክተኛውን የሚቃወም ሰው ሁሉ አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነው። (ከሓዲያን ሆይ)፣ ይህ ቅጣታችሁ ነው። እናም ቅመሱት። ለከሓዲያን የገሀነም እሳት ቅጣት በእርግጥ አለባቸው።

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-14) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የአላህ ፍራቻ በልባችን ውስጥ ሰርፆ መግባት እንዳለበት፤
2. እምነት በልብ ውስጥ ረግቶ የሚቀመጥ ብቻ ሳይሆን ሊጨምርና ሊቀንስ የሚችል ጉዳይ መሆኑን፤
3. የሙዕሚኖች የእምነት ደረጃ የሚለያይ መሆኑንና ከፊሉ አማኝ ሙሉ እምነት ሲሆን በከፊሉ ደግሞ እምነቱ ጎደሎ ስለ መሆኑ፤
4. ሙስሊሞችን ለታላቅ ድል ያበቃው የበድር ዘመቻ አጠቃላይ ሂደት ምን ይመስል እንደነበር የሚያሳይ ታሪካዊ ዘገባ፤

5. ሰዎች በተፈጥሮ መተግበር የሚቀላቸውን ነገር እንደሚወዱ፣
6. አላህ ምእመናን በሙሉ አደርገዋለሁ ብሎ ቃል የገባውን ነገር ያለምንም ጥርጥር ተግባራዊ ማድረጉንና መፈፀሙን፣
7. መንፈሳዊ እርዳታ መጠየቅ የሚቻለው ከአላህ ብቻ መሆኑንና እርዳታን የፈለገ ሰው ከአላህ ብቻ እንጂ ከሌላ ከማንኛውም አካል እርዳታን መጠየቅ የማይችል ስለመሆኑ፣
8. መላእክት የአላህ ባሪያዎች መሆናቸውንና አላህ ማንኛውንም አይነት ትዕዛዝ በፈለገው ወቅት ሊያዛቸው የሚችል ስለ መሆኑ፣
9. አላህ በበድር ዘመቻ ወቅት ለሙስሊሙ ኃይል መጠነ ሰፊ ውለታዎችን መዋሉና ሙስሊሞች ድል እንዲቀዳጁ የሚያስችሉ ጸጋዎችን እንዳፈሰሰባቸው፣
10. አላህንና ነብዩን (ﷺ) መንቀፍና መከራከር ድንጋጌዎቻቸውን መሞገት በምድራዊው ህይወትም ሆነ በአኼራ የሚያስቀጣ ወንጀል ስለ መሆኑ፣
11. አላህ ሙስሊሞች እንዴት አድርገው ጠላቶቻቸውን ቢዋጉ ሊያንበረክኳቸው እንደሚችሉ ያስተማራቸው ስለመሆኑ እንማራለን።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِذَا لَقِيتُمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ زَحْفًا فَلَا تُوَلُّوهُمُ ٱلْأَدْبَارَ ﴿١٥﴾ وَمَن يُوَلِّهِمْ يَوْمَئِذٍ دُبُرَهُۥٓ إِلَّا مُتَحَرِّفًا لِّقِتَالٍ أَوْ مُتَحَيِّزًا إِلَىٰ فِئَةٍ فَقَدْ بَآءَ بِغَضَبٍ مِّنَ ٱللَّهِ وَمَأْوَىٰهُ جَهَنَّمُ ۖ وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿١٦﴾

**15-16.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ እነዚያን በአላህ የካዱትን ሰዎች (ለጦር) ሲጓዙ ባገኛቿኋቸው ጊዜ ጀርባዎቻችሁን አታዙሩላቸው። ያን ጊዜ ለግድያ ለመዘዋወር ወይም ወደ ሰራዊት ለመቀላቀል ሳይሆን ጀርባውን የሚያዞርላቸው ሰው ሁሉ የአላህ ቁጣ ባለቤት ሆኑ። መኖሪያውም ገሀነም ናት። የገሀነም መመለሻነትም ከፋ።

فَلَمْ تَقْتُلُوهُمْ وَلَـٰكِنَّ ٱللَّهَ قَتَلَهُمْ ۚ وَمَا رَمَيْتَ إِذْ رَمَيْتَ وَلَـٰكِنَّ ٱللَّهَ رَمَىٰ ۚ وَلِيُبْلِىَ ٱلْمُؤْمِنِينَ مِنْهُ بَلَآءً حَسَنًا ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿١٧﴾

**17.** (አማኞች ሆይ)፣ እናንተ አልገደላቿኋቸውም። ግን አላህ ገደላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጭብጥን አፈር በወረወርክም ጊዜ አንተ አልወረወርክም። ግን አላህ ወረወረ። ምእመናን ሁሉ ከእርሱ የኾነን መልካም ፀጋ ለመስጠት ሲል (ይህን አደረገ)። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ፣ ለሚፈፅመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነውና።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (17) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የበድር ዘመቻ ዕለት ረሱል (ﷺ) አንድ ጭብጥ አፈር በእጃቸው ከዘገኑ በኋላ በጠላቶቻቸው (የሙሽሪኮች ሠራዊት)

ላይ ቢረጩት የአላህ ተዐምር ሆነና ከጠላቶች አንዱ እንኳን ሣይቀር በአይናቸውና በአፍንጫቸው ቀዳዳ ላይ አፈሩ እየገባ ስላጨናበሳቸው መፈርጠጡ ግዴታ ሆነባቸው። አላህም ይህንን ሁኔታ አስመልክቶ የእሱን ታምራዊነትና ድጋፍ የታከለበት መሆኑን አረጋገጠ። በዚህ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ذَٰلِكُمْ وَأَنَّ ٱللَّهَ مُوهِنُ كَيْدِ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿١٨﴾

**18.** ይህ (ዕውነት ነው)። አላህ የከሓዲያንን ተንኮል አድካሚ ነው።

إِن تَسْتَفْتِحُوا۟ فَقَدْ جَآءَكُمُ ٱلْفَتْحُ ۖ وَإِن تَنتَهُوا۟ فَهُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ ۖ وَإِن تَعُودُوا۟ نَعُدْ
وَلَن تُغْنِىَ عَنكُمْ فِئَتُكُمْ شَيْـًٔا وَلَوْ كَثُرَتْ وَأَنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٩﴾

**19.** (ከሓዲያን ሆይ)፣ ፍትሕን ብትጠይቁ ፍትሑ በእርግጥ መጥቶላችኋል። (ክሕደትንና መዋጋትን) ብትከለክሉም እርሱ ለእናንተ የተሻለ ነው። (ወደ መጋደል) ብትመለሱም እንመለሳለን። ሰራዊታችሁ ብትበዛም እንኳ ለእናንተ ምንም አትጠቅማችሁም። አላህ ሁልጊዜም ከትክክለኛ አማኞች ጋር ነውና።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች (19) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የበድር ዘመቻ ቀን ካፊሮችና ሙስሊሞች በተገናኙበት ጊዜ አቡጀህል ጌታዬ! የዘመድን መብት የቆረጠውንና የማይታወቅን ነገር ይዞ የመጣውን ሠው ከመሀላችን አይተህ መሬት አግባው ብሎ ስለ ለመነ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሃኪም፤ ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَطِيعُوا۟ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَا تَوَلَّوْا۟ عَنْهُ وَأَنتُمْ تَسْمَعُونَ ﴿٢٠﴾ وَلَا تَكُونُوا۟
كَٱلَّذِينَ قَالُوا۟ سَمِعْنَا وَهُمْ لَا يَسْمَعُونَ ﴿٢١﴾ ۞ إِنَّ شَرَّ ٱلدَّوَآبِّ عِندَ ٱللَّهِ ٱلصُّمُّ ٱلْبُكْمُ ٱلَّذِينَ
لَا يَعْقِلُونَ ﴿٢٢﴾ وَلَوْ عَلِمَ ٱللَّهُ فِيهِمْ خَيْرًا لَّأَسْمَعَهُمْ ۖ وَلَوْ أَسْمَعَهُمْ لَتَوَلَّوا۟ وَّهُم مُّعْرِضُونَ ﴿٢٣﴾

**20-23.** እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ። እናንተም እየሰማችሁ ከእርሱ አትሽሹ። እንደነዚያም የማይሰሙ ሲኾኑ ሰማን እንደ አሉት ሰዎች አትኹኑ። ከተንቀሳቃሾች ፍጡራን ሁሉ አላህ ዘንድ መጥፎ ተንኮለኞች ማለት እነዚያ (እውነትን) የማያውቁት (ሐቅን) የማይሰሙ ደንቆሮዎችና እውነትን የማይናገሩ ዲዳዎች ናቸው። በውስጣቸው ደግ መኖሩን አላህ ባወቀ ኖሮ የመረዳት መስማትን ያሰማቸው ነበር። ደግ የሌለባቸው መኾኑን እያወቀ ባሰማቸውም ኖሮ እነርሱ እውነትን የተው ሆነው በሸሹ ነበር።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱسْتَجِيبُواْ لِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ إِذَا دَعَاكُمْ لِمَا يُحْيِيكُمْ ۖ وَٱعْلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ
يَحُولُ بَيْنَ ٱلْمَرْءِ وَقَلْبِهِۦ وَأَنَّهُۥٓ إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ﴿٢٤﴾ وَٱتَّقُواْ فِتْنَةً لَّا تُصِيبَنَّ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ
مِنكُمْ خَآصَّةً ۖ وَٱعْلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿٢٥﴾ وَٱذْكُرُوٓاْ إِذْ أَنتُمْ قَلِيلٌ مُّسْتَضْعَفُونَ
فِى ٱلْأَرْضِ تَخَافُونَ أَن يَتَخَطَّفَكُمُ ٱلنَّاسُ فَـَٔاوَىٰكُمْ وَأَيَّدَكُم بِنَصْرِهِۦ وَرَزَقَكُم مِّنَ
ٱلطَّيِّبَـٰتِ لَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴿٢٦﴾

**24-26.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ መልዕክተኛው ሙሐመድ ህያው ወደ የሚያደርጋችሁ እምነት በጠራችሁ ጊዜ ለአላህና ለመልዕክተኛው ታዘዙ። አላህ በሰውየውና በልቡ መካከል የሚጋርድ መሆኑንና ወደ እርሱም የምትሰበሰቡ መሆናችሁን እወቁ። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ)፣ ከናንተ መካከል በመጨረሻ ውስጥ እነዚያን የበደሉትን ሰዎችን ብቻ ለይታ የማትጎዳን ፈተና ተጠንቀቁ። አላህ ቅጣቱ ብርቱ መሆኑን እወቁ። (እናንተ ከመካ ወደ መዲና የተሰደዳችሁ ሙስሊሞች ሆይ!) እናንተ በምድር ላይ የተናቃችሁ ጥቂቶች ኾናችሁ ሳላችሁ ሰዎች ሊነጥቁዋችሁ የምትፈሩ ስትኾኑ ያስጠጋችሁን በእርዳታውም ያበረታችሁን ከመልካሞች ሲሳዮችም ታመሰግኑ ዘንድ የሰጣችሁን አላህን ሁልጊዜ አስታውሱ።

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ከአንቀፅ ምዕራፍ (15-26) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

1. ከከሓዲያን ጦር ኃይል ጋር ከሚደረግ መስፈርቱ ከተሟላ የጂሃድ ጦርነት ግንባር መሸሽ ወንጀል ስለመሆኑ፤
2. አላህ የሰውን ልጅ እስከ ተግባሩ የፈጠረ ኃያል ጌታ ስለመሆኑ፤
3. በበድር ጦርነት ወቅት ነብዩ (ﷺ) በከሓዲያን ላይ የረጩት አዋራ በያንዳንዱ ከሃዲ አይን ውስጥ ገብቶ እንዲጨናበሱ በማድረግ አላህ ለረሱል የዋለላቸው ውለታ፤
4. አላህ የትክክለኛ አማኞችና የቅን አገልጋይ ባሪያዎቹ ወዳጅ ስለመሆኑ፤
5. የአላህ እና የመልዕክተኛው (ﷺ) ትዕዛዝ ያለምንም ማንገራገር መቀበልና መፈፀም ግዴታ ስለመሆኑ፤
6. ከአጋሪዎችና ከካፊሮች ከሓዲያን ጋር መንፈሳዊ ትስስር በመፍጠር የሚደረጉ መመሳሰሎች የተከለከሉ መሆኑን፤
7. ከሰዎች መካከል በአስተሳሰባቸው እጅግ የዘቀጡና ከእንስሳት በታች የሆነ ቦታ የሚሰጣቸውን አዕምሮ ቢሶች ስለ መኖራቸው፤
8. የአላህን እና የመልዕክተኛውን (ﷺ) ጥሪ በማክበር ተግባራዊ ምላሽ መስጠቱ የእያንዳንዱ ሙስሊም ግዴታ መሆኑን፤
9. በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል የኢስላምን ብርሃን ለህዝቡ ለማሳየት የሚችል ኢስላማዊ ግዳጅ መሆኑን፤
10. አላህ የዋለልንን ውለታዎች ማስታወሱና ፀጋዎችን መላልሶ ማስተንተኑ ያለውን ኢስላማዊ ፋይዳ እንማራለን።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَخُونُواْ ٱللَّهَ وَٱلرَّسُولَ وَتَخُونُوٓاْ أَمَٰنَٰتِكُمۡ وَأَنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ٢٧
وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّمَآ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَأَوۡلَٰدُكُمۡ فِتۡنَةٞ وَأَنَّ ٱللَّهَ عِندَهُۥٓ أَجۡرٌ عَظِيمٞ ٢٨

**27-28.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህንና መልዕክተኛውን አትካዱ። አደራዎቻችሁንም እናንተ እያወቃችሁ አትካዱ። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ ለፈተና ብቻ መሆናቸውንና አላህም ዘንድ ታላቅ ምንዳ ያለው መኾኑን ዕወቁ።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (27) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በኒ ቁረይዛዎችን ለማጥቃት (21) ቀን ከበባ አድርገው መውጫ መግቢያ ባሳጧቸው ጊዜ በኒ ቁረይዛዎች ከረሱል ሙሐመድ (ﷺ) ጋር ድርድር ለማድረግና ስምምነት ላይ ለመድረስ ጥያቄ አቀረቡ። ነብዩም (ﷺ) ሰዐድ ቢን ሙዐዝ በሚሰጡት ውሳኔ እንዲስማሙ ሀሳብ ሰነዘሩ። በኒ ቁረይዟዎች ግን የሰዐድ ቢን ሙዐዝን ውሳኔ ከመስማታችን በፊት አቡ ሉባባህ የተባሉ የቀድሞ ወዳጃቸውን እንዲልኩላቸው ጠየቁ። ረሱልም አቡ ሉባባህን ላኩላቸው። በኒ ቁረይዟዎችም ለአቡ ሉባባህ «በሰዕድ ቢን ሙአዝ ሀሳብ ብንስማማ ምን ይመስልሀል» ሲሉ ጠየቋቸው። በዚህ ጊዜ በምልክት ወደ ጉሮሮአቸው በማመላከት በሰዕድ ቢን ሙአዝ ውሳኔ ከተስማሙ የሚጠብቃቸው ሞት መሆኑን በመግለፅ ካስጠነቀቋቸው በኋላ ተፀፀቱ። ወዲያውም በመስጊድ ውስጥ ባሉ ቋሚ ምሰሶዎች ራሳቸውን አስረው አልበላም አልጠጣም በማለት ሰባት ቀናት አሳለፉ። በጣም ስለተዳከሙና ስለተጐሳቆሉ ነብዩ (ﷺ) «ከአላህ ተውበት እንደመጣለት ንገሩት» በማለት ላኩባቸው አቡ ሉባባ ግን ወላሂ ራሴን አልፈታም ነብዩ (ﷺ) እስካልፈቱኝ ድረስ በማለት በአቋማቸው ፀኑ። ነብዩ (ﷺ) ይህ ሲነገራቸው መጥተው በእጃቸው ፈቷቸው። አቡ ሉባባ ወደ አላህ ከመቶበቴ ምልክቶች አንዱ ይህን ወንጀል የፈፀምኩባትን አገር ለቆ መሄድና ንብረቴንም በሙሉ ለአላህ መስጠት ነው ሲሉ ነብዩ (ﷺ) አንድ ሦስተኛውን መስጠት ይበቃሃል አሏቸው። ይህን ታሪክ ምክንያት በማድረግ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِن تَتَّقُواْ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّكُمۡ فُرۡقَانٗا وَيُكَفِّرۡ عَنكُمۡ سَيِّـَٔاتِكُمۡ
وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡۗ وَٱللَّهُ ذُو ٱلۡفَضۡلِ ٱلۡعَظِيمِ ٢٩

**29.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!፣ አላህን ብትፈሩ የእውነት መለያን ብርሃንን ያደርግላችኋል። ክፉ ሥራዎቻችሁንም ከናንተ ላይ ያብስላችኋል። ለእናንተም ይምራችኋል። አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነውና።

وَإِذۡ يَمۡكُرُ بِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِيُثۡبِتُوكَ أَوۡ يَقۡتُلُوكَ أَوۡ يُخۡرِجُوكَۚ وَيَمۡكُرُونَ وَيَمۡكُرُ ٱللَّهُۖ
وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلۡمَٰكِرِينَ ٣٠

**30.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሊያስሩህ ወይም ሊገድሉህ ወይም ከመካ ሊያስወጡህ በአንተ ላይ በመከሩብህ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ይመክራሉም። አላህም ተንኮላቸውን ይመልስባቸዋል። አላህ ግን ከመካሪዎቹ ሁሉ በላይ ነውና።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (30) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- መኮች የነብዩ (ﷺ) ጉዳይ አሳስቧቸው ነብይ በሆኑ በ (14) ዓመት በዳረል ነድዋ አንድ ወሳኝ ስብሰባ አደረጉ። በተለይም የዳዕዋው ባለቤት ነብዩ መካ ውስጥ ያሉ ቢሆንም በአንድ ምሽት ወይም ረፋድ ላይ ወደ ሀበሻ ወይም መዲና ሊወጡ ይችላሉ ተብሎ ይፈራ ነበር። በስብሰባው ላይ ታላላቅ የቁረይሽ ሽማግሌዎች እና ሹማምንት ተገኝተው ነበር። ኢብሊስም ከቆላማ በረሃ አካባቢ የመጣ ሽማግሌ በመምሰል ለስብሰባው አንገብጋቢነት ተጨንቆና ተጠቦ የመጣ መሆኑን በመንገር አሰፈቅዷቸው። ስብሰባው ላይ ተገኘ። ስብሰባውም ተከፈተ። ውይይቱ ተጀመረ። አቡ አስወድ የተባለ ሽማግሌ «ምን ያስጨንቃል ከምድራችን አስወጥተነው የራሳችንን ህይወት እንምራ። እናስተካክል። የትም ቢሄድ ግድ የለንም» በማለት ሃሳቡን ሲሰነዝር «ኢብሊስ የዚህን ሰው አንደበት ጥፍጥናና ርቱዕነት፤ የሰዎችን ልብ እንዴት ማሸነፍ እንደሚችል እና አደገኛ ሰባኪ እንደሆነ አይታችሁታል? ከዚህ ከወጣ አንድ አረብ ሀገር በመሄድ ብዙ ሰዎችን ያፈራና ተመልሶ ይወራችኋል። እና ሌላ ሃሳብ ብታቀርቡ ይሻላችኋል» በማለት ሃሳቡን ተቃወመው። አቡል ቡኽቱሪ የተባለ ሽማግሌ «እሰሩትና በር ዝጉበት። ከእርሱ በፊት የነበሩ ገጣሚዎች ያጋጠማቸውን ሞት እስከሚያገኘው ድረስ ተዘግቶ ይኑር» በማለት ሃሳብ አቀረቡ። ኢብሊስ «ብታስሩትም ጓደኞቹ በጣም ይሰሙታል። ከአባቶቻቸውና ከልጆቻቸው ያስበልጡታል። በአንድ ጊዜ ወረዋችሁ ከእጃችሁ ያስወጡታል። በመቀጠልም ብቀላቸው አያሌ እልቂቶችን ያስከትላል። ሌላ ሃሳብ አምጡ» አላቸው። በዚህን ጊዜ አቡ ጀህል «እኔ ጥሩ ሀሳብ አለኝ። እሱም ከእያንዳንዱ ጎሳ ጠንካራ የሆነ ወጣት እንምረጥ። ለሁሉም በጣም ስለታም ጐራዴዎችን እንስጣቸውና በአንድ ጊዜ ይምቱትና ይግደሉት» አለ። በዚህ መልኩ «ደሙ በየጎሳዎቹ ውስጥ ከተበታተነ የሡ ዘመዶች ከቁረይሽ ብሔር ጋር መዋጋት ስለማይችሉ ሳይወዱ በግዳቸው የደም ካሳ ይቀበላሉ። ካሳውን እንሰጣቸዋለን። በሰላም እንኖራለን» በማለት ሃሳቡን ሲያቀርብ የተንኮለኞቹ አለቃ ኢብሊስም «ይህ ነው እኔ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ሃሳብ። ከዚህ የበለጠ ምንም ሃሳብ ሊኖር አይችልም» አለ። ጅብሪልም የስብሰባውን ሁኔታ በሙሉ አምጥቶ ለነብዩ (ﷺ) በማድረስ ዕለቷን ቤታቸው እንዳያድሩና ወደ መዲና መሰደድም እንደተፈቀደላቸው ተነገራቸው። ይህን ታሪክ ለማስታወስ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُنَا قَالُواْ قَدۡ سَمِعۡنَا لَوۡ نَشَآءُ لَقُلۡنَا مِثۡلَ هَٰذَآ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّآ أَسَٰطِيرُ
ٱلۡأَوَّلِينَ ٣١ وَإِذۡ قَالُواْ ٱللَّهُمَّ إِن كَانَ هَٰذَا هُوَ ٱلۡحَقَّ مِنۡ عِندِكَ فَأَمۡطِرۡ عَلَيۡنَا حِجَارَةٗ
مِّنَ ٱلسَّمَآءِ أَوِ ٱئۡتِنَا بِعَذَابٍ أَلِيمٖ ٣٢ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيُعَذِّبَهُمۡ وَأَنتَ فِيهِمۡۚ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ
مُعَذِّبَهُمۡ وَهُمۡ يَسۡتَغۡفِرُونَ ٣٣

**31-33.** አንቀፆቻችን በነሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ በእርግጥ ሰምተናል በሻን ኖሮ የዚህን አባባል ተመሳሳይ ባልን ነበር። ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታችን ሆይ፤ ይህ እርሱ ከአንተ ዘንድ የተወረደ እውነት እንደኾነ በእኛ ላይ ከሰማይ ድንጋዮችን አዝንምብብን ወይም አሳማሚ ቅጣትን አምጣብን ባሉ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህም አንተ በውስጣቸው እያለህ ድንጋይ በማዝነብና ባሳማሚ ቅጣት የሚቀጣቸው አይደለም። እንደዚሁም አላህ እነርሱ ምሕረትን የሚለምኑት ሲኾኑ የሚቀጣቸው አይደለም።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ ከ (31-33) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ ነብዩ (ﷺ) የበድር ዕለት ከማረኳቸው እና ሞት ከተፈረደባቸው ሰዎች መካከል ኡቅበት ኢብኑ አቡ ሙአይጥ ጡዐይመት፤ ኢብኑ አዲይ እና ሚቅዳድ ማርኮት የነበረው ነድር ኢብኑል ሀሪስ ይገኙበት ነበር። ታዲያ እሱ እንዲገድል በታዘዘ ጊዜ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ምርኮኛዬን» በማለት ሲጠይቅ «አዎ እሱ እኮ ስለ ቁርኣን ብዙ ያለ ሰው ነው» በማለት መለሡለት። ከዚያም እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። (ጦበሪ፤ ሱዩጢ እና ዋሒዲ)

وَمَا لَهُمْ أَلَّا يُعَذِّبَهُمُ ٱللَّهُ وَهُمْ يَصُدُّونَ عَنِ ٱلْمَسْجِدِ ٱلْحَرَامِ وَمَا كَانُوٓاْ أَوْلِيَآءَهُۥٓ ۚ إِنْ أَوْلِيَآؤُهُۥٓ إِلَّا ٱلْمُتَّقُونَ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٤﴾ وَمَا كَانَ صَلَاتُهُمْ عِندَ ٱلْبَيْتِ إِلَّا مُكَآءً وَتَصْدِيَةً ۚ فَذُوقُواْ ٱلْعَذَابَ بِمَا كُنتُمْ تَكْفُرُونَ ﴿٣٥﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُنفِقُونَ أَمْوَٰلَهُمْ لِيَصُدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ ۚ فَسَيُنفِقُونَهَا ثُمَّ تَكُونُ عَلَيْهِمْ حَسْرَةً ثُمَّ يُغْلَبُونَ ۗ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِلَىٰ جَهَنَّمَ يُحْشَرُونَ ﴿٣٦﴾ لِيَمِيزَ ٱللَّهُ ٱلْخَبِيثَ مِنَ ٱلطَّيِّبِ وَيَجْعَلَ ٱلْخَبِيثَ بَعْضَهُۥ عَلَىٰ بَعْضٍ فَيَرْكُمَهُۥ جَمِيعًا فَيَجْعَلَهُۥ فِى جَهَنَّمَ ۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿٣٧﴾

**34-37.** እነርሱ ከተከበረው መስጊድ የሚከለክሉ ሲሆኑ አላህ (በሰይፍ) የማይቀጣቸው ለመሆኑ ለእነርሱ ምን ዋስትና አላቸው። የቤቱ ጠባቂዎቹ አልነበሩም። ጠባቂዎቹ ክሕደትን ተጠንቃቂዎቹ እንጂ ሌሎቹ አይደሉም። ግን አብዛኛዎቹ ይህን እውነታ አያውቁም። በከዕባ ውስጥ ስግደታቸው ማፏጨትና ማጨብጨብ እንጂ ሌላ አልነበረም። ትክዱት በነበራችሁትም ነገር ቅጣትን ቅመሱ (ይባላሉ)። እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ ከአላህ መንገድ ሰዎችን ሊከለክሉ ገንዘቦቻቸውን ያወጣሉ። በእርግጥም ያወጡታል። ከዚያ ግን በእነርሱ ላይ ፀፀት ይሆንባቸዋል። ከዚያ ይሸነፋሉ። እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ ወደ ገሀነም ይሰበሰባሉ። አላህ መጥፎውን ነገር ከመልካሙ ሊለይ መጥፎውንም ከፊሉን በከፊሉ ላይ ሊያደርግና ባንድ ላይ ሊያነባብረው በገሀነም ውስጥም ሊያደርገው (ይሰበሰባሉ)። እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎቹ ናቸው።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች (35) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ የመካ ሰወች ጠዋፍ ሲያደርጉ ያጨበጭቡና ያፏጨ ስለነበር ይህን ተግባራቸውን ለማውገዝ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑል ጀውዚ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (27-37) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

1. የትኛውንም ሰው መካድ ቃልን ማፍረስ በቀጠሮ አለመገኘት የተከለከለ ከመሆኑ ጋር አላህንና ረሱል (ﷺ) መካዱ እጅግ የተወገዘ ክልክልነቱም በጣም የጠነከረ ስለመሆኑ፤

2. ገንዘብና ልጅ እጅግ የሚያሳሱና የሚያጓጉ በመሆናቸው ከአላህ ጋር ሊያጣሉ የሚችሉ ከኢስላማዊ ትዕዛዛትም ሊያዘናጉ የሚችሉ ስለሆኑ መጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን፤
3. አላህን መፍራት ለወንጀል ምህረትን እንደሚያሰጥና ወደ እውነት የሚያደርስ ብርሃን እንደሚያስጨብጥ፤
4. አላህ ለመልዕክተኛው ከዋለላቸው መጠነ ሰፊ ውለታዎች መሀከል ከፊሉን የሚያወሳ ቁርአናዊ አንቀፅ፤
5. ቁረይሽ ጣኦታዊያን የኢስላምን ብርሃን የሚረጨውን የነብዩን (ﷺ) ዳዕዋ ለማደናቀፍ የፈጸሙት ተንኮልና የሸረቡት ሴራ ምን ያህል የከፋ እንደነበር፤
6. የመካ ጣኦታዊያን ለእውነት የነበራቸው ጥላቻ ምን ያህል ስር የሰደደ እንደነበርና ባጢልን ናፋቂ እንደነበሩ፤
7. ኃጢአትን አውቆ ከወንጀል ለመፅዳት ይቅርታ መጠየቅ ወንጀልን ከማሠረዝ አልፎ ታላቅ የሆነ ምንዳ የሚያስገኝ ተግባር መሆኑን፤
8. ሰዎች ወደ አላህ ቤት እንዳይቀርቡ መከልከል ምን ያህል ከባድ ወንጀል መሆኑን፤
9. መስጂዶችን የመንከባከብና የማስተዳደር ኃላፊነት ሊሠጣቸው የሚገባው ለአላህ ወዳጆች ብቻ ስለመሆኑ፤
10. ማጨብጨብና ማፏጨት የተጠሉ ባህርያት ስለመሆናቸውና በዒባዳ (አላህን በመገዛት) ወቅት ተገቢ ያለመሆናቸው እንማራለን።
11. ከአላህ መንገድ ሰዎችን ለመከላከል፤ የኢስላምን ጉዞ ለማደናቀፍ የሚለገሱ ገንዘቦች የቂያማ (የትንሳኤ) እለት በከፋዩ ላይ ፀፀትን እንደሚያስከትሉ፤
12. ከሓዲያን ባጠቃላይ መጥፎዎች ተብለው ሊፈረጁ የሚችሉ መሆኑንና በአንፃሩም አማኞች ባጠቃላይ መልካም ሰዎች ተብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ፤
13. የአላህ ቃል እውነተኛና ቅንጣት ታህል ሀሰት ያልተቀላቀለበት መሆኑ የተረጋገጠ ሀቅ እንደሆነ እንማራለን።

قُل لِّلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِن يَنتَهُواْ يُغۡفَرۡ لَهُم مَّا قَدۡ سَلَفَ وَإِن يَعُودُواْ فَقَدۡ مَضَتۡ سُنَّتُ
ٱلۡأَوَّلِينَ ٣٨ وَقَٰتِلُوهُمۡ حَتَّىٰ لَا تَكُونَ فِتۡنَةٞ وَيَكُونَ ٱلدِّينُ كُلُّهُۥ لِلَّهِۚ فَإِنِ ٱنتَهَوۡاْ فَإِنَّ ٱللَّهَ
بِمَا يَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ٣٩ وَإِن تَوَلَّوۡاْ فَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ مَوۡلَىٰكُمۡۚ نِعۡمَ ٱلۡمَوۡلَىٰ وَنِعۡمَ ٱلنَّصِيرُ ٤٠

**38-40.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነዚያ በአላህ ለካዱት ቢከለከሉ ለእነርሱ በእርግጥ ያለፈውን ሥራ ምሕረት ይደረግላቸዋል። ወደ መጋደል ቢመለሱም (እናጠፋቸዋለን)። የቀድሞዎቹ ሕዝቦች (ልማድ) ሲያጠፉ መጠፋት በእርግጥ አልፏልና በላቸው። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ)፣ ሁከት እስከሚጠፋና ሃይማኖት ሁሉ ለአላህ ብቻ እስከሚሆን ድረስ ተጋደሏቸው። ቢከለከሉም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነው*። ከእምነት ቢዞሩም አላህ ረዳታችሁ መሆኑን እወቁ። እርሱ ምን ያምር ጠባቂ!፣ ምን ያምርም ረዳት ነው!።

✷ አላህ ለሰዎች የመረጠው ትክክለኛው መንገድ ኢስላም ነው። ወደፊት የዐለም መጨረሻም ሲደርስ ወደ ዚህ ዐለም የሚመጡት ነብዩ ዒሳ ምን እንደሚሰሩ የአላህ መልዕክተኛ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ፤ የመርየም ልጅ ዒሳ በናንተ ላይ ፍትሐዊ መሪ ሆኖ ይወርዳል። መስቀልንም ይሰብራል። አሳማዎችን ይገድላል። ጃዝያህን ሙስሊም ያልሆኑ ወገኖች ለሙስሊም መንግስታት የሚሰጧቸውን የመኖሪያ ግብር ያጠፋል። ገንዘብን የሚቀበል አንድም ድሃ እስከማይኖር ድረስ ገንዘብ ይበረክታል»

۞ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّمَا غَنِمۡتُم مِّن شَيۡءٖ فَأَنَّ لِلَّهِ خُمُسَهُۥ وَلِلرَّسُولِ وَلِذِي ٱلۡقُرۡبَىٰ وَٱلۡيَتَٰمَىٰ
وَٱلۡمَسَٰكِينِ وَٱبۡنِ ٱلسَّبِيلِ إِن كُنتُمۡ ءَامَنتُم بِٱللَّهِ وَمَآ أَنزَلۡنَا عَلَىٰ عَبۡدِنَا يَوۡمَ ٱلۡفُرۡقَانِ يَوۡمَ
ٱلۡتَقَى ٱلۡجَمۡعَانِۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ٤١

**41.** ✷(እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ከማንኛውም ነገር በጦር ከካሐዲያን የማረካችሁትም አንድ አምስተኛው ለአላህና ለመልዕክተኛው ለነብዩ የዝምድና ባለቤቶችም ለየቲሞችም ለሚስኪኖችም ለመንገደኞችም የተገባ መሆኑን እወቁ። በአላህና በዚያም እውነትና ውሸት በተለየበት ቀን ሁለቱ ቡድኖች በተገናኙበት በበድር ቀን ባገልጋያችን ላይ ባወረድነው የምታምኑ እንደ ሆናችሁ ይህንን እወቁ። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

✷ ክፍል አስር

إِذۡ أَنتُم بِٱلۡعُدۡوَةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُم بِٱلۡعُدۡوَةِ ٱلۡقُصۡوَىٰ وَٱلرَّكۡبُ أَسۡفَلَ مِنكُمۡۚ وَلَوۡ تَوَاعَدتُّمۡ
لَٱخۡتَلَفۡتُمۡ فِي ٱلۡمِيعَٰدِ وَلَٰكِن لِّيَقۡضِيَ ٱللَّهُ أَمۡرٗا كَانَ مَفۡعُولٗا لِّيَهۡلِكَ مَنۡ هَلَكَ عَنۢ بَيِّنَةٖ
وَيَحۡيَىٰ مَنۡ حَيَّ عَنۢ بَيِّنَةٖۗ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَسَمِيعٌ عَلِيمٌ ٤٢

**42.** (ሙስሊሞች ሆይ!) እናንተ በቅርቢቱ ዳርቻ ሁናችሁ እነርሱ ደግሞ በሩቂቱ ዳርቻ ኾነው የነጋዴዎቹም ቡድን ከናንተ በታች ሲኾኑ በሰፈራችሁ ጊዜ ያደረግንላችሁን (አስታውሱ)። በተቃጠራችሁ ኖሮ ግን በቀጠሮው በተለያያችሁ ነበር። ግን አላህ ሊሠራው የሚገባውን ነገር ሊፈጽምና የሚጠፋ ሰውም ከአስረጅ መድረስ በኋላ እንዲጠፋ ሕያው የሚሆንም ሰውም ከአስረጅ መድረስ በኋላ ሕያው እንዲሆን ያለቀጠሮ አጋጠማችሁ። አላህ በእርግጥ ሰሚና ዐዋቂ ነውና።

إِذۡ يُرِيكَهُمُ ٱللَّهُ فِي مَنَامِكَ قَلِيلٗاۖ وَلَوۡ أَرَىٰكَهُمۡ كَثِيرٗا لَّفَشِلۡتُمۡ وَلَتَنَٰزَعۡتُمۡ فِي ٱلۡأَمۡرِ
وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ سَلَّمَۚ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٤٣ وَإِذۡ يُرِيكُمُوهُمۡ إِذِ ٱلۡتَقَيۡتُمۡ فِيٓ أَعۡيُنِكُمۡ
قَلِيلٗا وَيُقَلِّلُكُمۡ فِيٓ أَعۡيُنِهِمۡ لِيَقۡضِيَ ٱللَّهُ أَمۡرٗا كَانَ مَفۡعُولٗاۗ وَإِلَى ٱللَّهِ تُرۡجَعُ ٱلۡأُمُورُ ٤٤

**43-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሕልምህ እነርሱን ጥቂት አድርጎ ባሳየህ ጊዜ (አስታውስ)። እነርሱን ብዙ አድርጎ ባሳየህም ኖሮ በፈራችሁና በነገሩ በተጨቃጨቃችሁ ነበር ግን አላህ አዳናችሁ። እርሱ በደረቶች ውስጥ ያለን ሁሉ ዐዋቂ ነውና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ሊሠራው የሚገባን ነገር ይፈጽም ዘንድ በተጋጠማችሁ ጊዜ ጥቂት አድርጎ ያሳየህንና በዓይኖቻቸውም ላይ እናንተን ያሳነሳችሁን (አስታውሱ)። ነገሮቹም ሁሉ ወደ አላህ ብቻ ይመለሳሉ።

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (38-44) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

1. የአላህ ፈድል (ስጦታ) እጅግ የሰፋና ብዙ ስለመሆኑ፤
2. እምነት ዘወትር ሊታደስና ሊታወስ የሚገባ የህይወት ትልቁ አስፈላጊ ጉዳይ ስለመሆኑ፤
3. የበድር ዘመቻ ሙስሊሞች ታላቅ ድል ያገኙበት ታሪካዊና ታላቅ ዘመቻ እንደነበር፤
4. የአላህ ቀን አገልጋዮችና ወዳጆቹ አነማን እንደሆኑ፤
5. ኢስላምን የተቀበለ ሰው ከኢስላም በፊት የሰራቸውን ወንጀሎች ባጠቃላይ ኢስላም የሚያስርዝለት ስለ መሆኑ፤
6. አጋሪዎችን ማውገዝ ሕገ ወጥ ድርጊቶቻቸውን በሕዝብ ላይ እንዳይረጩ መታገልና መዋጋት በሙስሊሞች ላይ የተጣለ ግዴታ ስለመሆኑ፤
7. በምርኮ የተገኘ ንብረት ለሙስሊሙ ህብረተሰብ በአግባቡ ሊከፋፈል የሚገባ የሙስሊሞች የጋራ ሀብት መሆኑንና እንዴት እንደሚከፋፈል እንማራለን።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا لَقِيتُمْ فِئَةً فَٱثْبُتُواْ وَٱذْكُرُواْ ٱللَّهَ كَثِيرًا لَّعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٤٥﴾ وَأَطِيعُواْ
ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَا تَنَـٰزَعُواْ فَتَفْشَلُواْ وَتَذْهَبَ رِيحُكُمْ ۖ وَٱصْبِرُوٓاْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلصَّـٰبِرِينَ ﴿٤٦﴾

**45-46.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ሰራዊትን በገጠማችሁ ጊዜ እርጉ (መክቱ)። አላህንም በብዙ አውሱ በእርግጥ ትድናላችሁና። (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ። አትጨቃጨቁም ትፈራላችሁና ኃይላችሁም ትኼዳለችና። ታገሡም አላህ በእርዳታው ከትዕግሥተኞች ጋር ነውና።

وَلَا تَكُونُواْ كَٱلَّذِينَ خَرَجُواْ مِن دِيَـٰرِهِم بَطَرًا وَرِئَآءَ ٱلنَّاسِ وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ ۚ
وَٱللَّهُ بِمَا يَعْمَلُونَ مُحِيطٌ ﴿٤٧﴾ وَإِذْ زَيَّنَ لَهُمُ ٱلشَّيْطَـٰنُ أَعْمَـٰلَهُمْ وَقَالَ لَا غَالِبَ لَكُمُ ٱلْيَوْمَ
مِنَ ٱلنَّاسِ وَإِنِّى جَارٌ لَّكُمْ ۖ فَلَمَّا تَرَآءَتِ ٱلْفِئَتَانِ نَكَصَ عَلَىٰ عَقِبَيْهِ وَقَالَ إِنِّى بَرِىٓءٌ
مِّنكُمْ إِنِّىٓ أَرَىٰ مَا لَا تَرَوْنَ إِنِّىٓ أَخَافُ ٱللَّهَ ۚ وَٱللَّهُ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ﴿٤٨﴾

**47-48.** እንደእነዚያ ለትዕቢትና ለሰዎች ይዩልኝ ሲሉ ከአላህም መንገድ ለማገድ ከአገራቸው እንደወጡት ሰዎች አትሁኑ። አላህ በሚሠሩት ሁሉ (በእውቀቱ) ከባቢ ነውና። ሰይጣንም ሥራዎቻቸውን ለእነርሱ ባሳመረላቸውና ዛሬ ለእናንተ ከሰዎች አሸናፊ የላችሁም። እኔም ለእናንተ ረዳት ነኝ ባለ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ሁለቱ ጭፍሮችም በተያዩ ጊዜ ወደኋላው አፈገፈገ። እኔ ከናንተ ንፁህ ነኝ። እኔ እናንተ የማታዩትን አያለሁ። እኔ አላህን እፈራለሁ። አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነው አላቸውም።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (47) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የበድር ዘመቻ ቀን ቁረይሾች ከመካ ሲወጡ በዘፋኞችና በድቤ ታጅበው ስለነበረ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ሱዩጢ)

إِذۡ يَقُولُ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ وَٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٌ غَرَّ هَٰٓؤُلَآءِ دِينُهُمۡۗ
وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَإِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٤٩﴾

**49.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ሰዎች እነዚህን (ሙስሊሞች) ሃይማኖታቸው አታለላቸው ባሉ ጊዜ (የነበረውን አስታውስ)። በአላህ ላይ የሚጠጋ ሁልጊዜም ያሸንፋል። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (49) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በመካ በሱረቱል ቀመር ውስጥ (45) ቁጥር (አንቀፅ) ላይ የተዘገበውን ቡድን ኡመር ኢብኑል ኸጣብ «የትኛው ቡድን ነው» ብለው ጠይቀው ነበር። ጥያቄያቸው መልስ ሳያገኝ የበድር ዘመቻ እለት ከሓዲዎች ተሸንፈው ሙስሊሞች ከኋላቸው እያሳደዷቸው ባሉበት ሰዐት ነብዩም (ﷺ) ይህኑ አንቀፅ ሲያነቡ ሰማኋቸውና ቡድን የተባለው ማን እንደሆነ ተረዳሁ። በዚህም ምክንያት ይህ አንቀፅ ወረደ። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَلَوۡ تَرَىٰٓ إِذۡ يَتَوَفَّى ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَضۡرِبُونَ وُجُوهَهُمۡ وَأَدۡبَٰرَهُمۡ وَذُوقُواْ عَذَابَ
ٱلۡحَرِيقِ ﴿٥٠﴾ ذَٰلِكَ بِمَا قَدَّمَتۡ أَيۡدِيكُمۡ وَأَنَّ ٱللَّهَ لَيۡسَ بِظَلَّٰمٖ لِّلۡعَبِيدِ ﴿٥١﴾ كَدَأۡبِ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ
وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ فَأَخَذَهُمُ ٱللَّهُ بِذُنُوبِهِمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ قَوِيٌّ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ﴿٥٢﴾

**50-52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን በአላህ የካዱትን ሰዎች መላዕክት ፊቶቻቸውንና ጀርባቸውን እየመቱ የቃጠሎንም ስቃይ ቅመሱ (እያሉ) በሚገድሏቸው ጊዜ ብታይ ኖሮ (አስደንጋጭን ነገር ታይ ነበር)። ይህ እጆቻችሁ ባስቀደሙት ምክንያት አላህ ለባሮቹ በዳይ ባለመኾኑ ነው (ይባላሉ)። የእነዚያ ሰዎች ልማድ እንደ ፈርዖን ቤተሰብና እንደነዚያም ከእነርሱ በፊት እንደ ነበሩት ልማድ ነው። በአላህ አንቀፆች ካዱ። አላህ በኃጢአቶቻቸው ያዛቸው። አላህ ሀይለኛ፣ ቅጣተ ብርቱ ነውና።

ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ لَمۡ يَكُ مُغَيِّرٗا نِّعۡمَةً أَنۡعَمَهَا عَلَىٰ قَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡ
وَأَنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ٥٣

**53.** ይህ (ቅጣት) አላህ በሕዝቦች ላይ የለገሰውን ፀጋ በነፍሶቻቸው ያለውን ነገር እስከሚለውጡ ድረስ የማይለውጥ በመሆኑ ምክንያት ነው። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፅመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነው።

كَدَأۡبِ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ وَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمۡ فَأَهۡلَكۡنَٰهُم بِذُنُوبِهِمۡ وَأَغۡرَقۡنَآ
ءَالَ فِرۡعَوۡنَۚ وَكُلّٞ كَانُواْ ظَٰلِمِينَ ٥٤

**54.** እንደ ፈርዖን ቤተሰቦችና እንደእነዚያም ከእነርሱ በፊት እንደ ነበሩት የአመጽ ልማድ (እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥባቸውም) በጌታቸው ታምራት አስተባበሉና በኃጢአቶቻቸው አጠፋናቸው። የፈርዖንን ቤተሰቦች አስመጥናቸው። ሁሉም በዳዮች ነበሩ።

إِنَّ شَرَّ ٱلدَّوَآبِّ عِندَ ٱللَّهِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ٥٥ ٱلَّذِينَ عَٰهَدتَّ مِنۡهُمۡ ثُمَّ يَنقُضُونَ
عَهۡدَهُمۡ فِي كُلِّ مَرَّةٖ وَهُمۡ لَا يَتَّقُونَ ٥٦ فَإِمَّا تَثۡقَفَنَّهُمۡ فِي ٱلۡحَرۡبِ فَشَرِّدۡ بِهِم مَّنۡ خَلۡفَهُمۡ لَعَلَّهُمۡ
يَذَّكَّرُونَ ٥٧ وَإِمَّا تَخَافَنَّ مِن قَوۡمٍ خِيَانَةٗ فَٱنۢبِذۡ إِلَيۡهِمۡ عَلَىٰ سَوَآءٍۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلۡخَآئِنِينَ ٥٨

**55-58.** ከሚንቀሳቀሱ እንስሳዎች ሁሉ አላህ ዘንድ ይበልጥ ከፉዎቹ እነዚያ ዘወትር በአላህ የካዱት ሰዎች ናቸው። ስለዚህ እነርሱ አያምኑም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ ከእነርሱ ቃል ኪዳን የያዝክባቸውና ከዚያ በየጊዜው ቃል ኪዳናቸውን የሚያፈርሱ ናቸው። እነርሱም አይጠነቀቁም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በጦርም ላይ ብታገኛቸው በእነርሱ ቅጣት ምክንያት ሌሎቹ ከሓዲዎች ይገሰጹ ዘንድ ከኋላቸው ያሉትን በትንባቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሕዝቦች በኩል ክህደትን ብትፈራ የቃል ኪዳኑን መፍረስ በማወቅ በመተካከል ላይ ሆናችሁ ቃል ኪዳናቸውን ወደ እነርሱ ጣልላቸው። አላህ ከዳተኞችን አይወድምና።

*በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (58) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከአህዛብ ዘመቻ እንደተመለሡ የጦር መሣሪያቸውን አውልቀው ባሉበት ጅብሪል መጥቶ ሙሐመድ! መሣሪያ አስቀመጥክ እንዴ እኔ እኮ ሠዎችን ከማሣደድ አላረፍኩም በል ተነስና ውጣ አላህ በኒ ቁረይዟዎችን ፈቅዶልሀልና በማለቱ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)*

وَلَا يَحْسَبَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ سَبَقُوٓاْ إِنَّهُمْ لَا يُعْجِزُونَ ﴿٥٩﴾ وَأَعِدُّواْ لَهُم مَّا ٱسْتَطَعْتُم مِّن قُوَّةٍ وَمِن رِّبَاطِ ٱلْخَيْلِ تُرْهِبُونَ بِهِۦ عَدُوَّ ٱللَّهِ وَعَدُوَّكُمْ وَءَاخَرِينَ مِن دُونِهِمْ لَا تَعْلَمُونَهُمُ ٱللَّهُ يَعْلَمُهُمْ ۚ وَمَا تُنفِقُواْ مِن شَيْءٍ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ يُوَفَّ إِلَيْكُمْ وَأَنتُمْ لَا تُظْلَمُونَ ﴿٦٠﴾ ۞ وَإِن جَنَحُواْ لِلسَّلْمِ فَٱجْنَحْ لَهَا وَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٦١﴾

**59-61.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ከአላህ ቅጣት ያመለጡ መኾናቸውን አያስቡ። እነርሱ አያቅቱምና (አያሸንፉምና)። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) ለእነርሱ ከማንኛው ኃይልና ከታጀቡ ፈረሶች የቻላችሁትን ሁሉ በእርሱ የአላህን ጠላትና ጠላታችሁን ሌሎችንም ከእነርሱ በቀር ያሉትን የማታውቋቸውን አላህ የሚያውቃቸውን (መናፍቃን) የምታስፈራሩበት ስትሆኑ አዘጋጁላቸው። ከማንኛውም ነገር በአላህ መንገድ የምትለግሱት ምንዳው ወደ እናንተ በሙሉ ይሰጣል። እናንተም ቅንጣት አትበደሉም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ ዕርቅ ቢያዘነብሉ አንተም ወደ ዕርቁ ተዘንበል እና በአላህ ላይ ብቻ ተመካ። እነሆ እርሱ ሁሉን ሰሚ እና ሁሉን ዐዋቂ ነውና።

وَإِن يُرِيدُوٓاْ أَن يَخْدَعُوكَ فَإِنَّ حَسْبَكَ ٱللَّهُ ۚ هُوَ ٱلَّذِىٓ أَيَّدَكَ بِنَصْرِهِۦ وَبِٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٦٢﴾ وَأَلَّفَ بَيْنَ قُلُوبِهِمْ ۚ لَوْ أَنفَقْتَ مَا فِى ٱلْأَرْضِ جَمِيعًا مَّآ أَلَّفْتَ بَيْنَ قُلُوبِهِمْ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ أَلَّفَ بَيْنَهُمْ ۚ إِنَّهُۥ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٦٣﴾

**62-63.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሊያታልሉህ ቢፈልጉ አላህ በቂህ ነው። እርሱ ያ፣ በእርዳታውና በምዕምናን ያበረታህ ነውና። አላህ በእነርሱ መካከል ያስማማ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ያለውን ሁሉ ሀብት ብትለገስ ኖሮ እንኳን በልቦቻቸው መካከል ባላስማማህ ነበር። ግን አላህ በመካከላቸው አስማማ። እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (45-63) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ለድል የሚያበቁ ምክንያቶች ምን ምን እንደሆኑና በአንፃሩም ለሽንፈት የሚያበቁ ደግሞ የትኞቹ ነገሮች እንደሆኑ፤
2. ሰይጣን የካፊሮችን ልብ በመቆጣጠር እንዴት አድርጎ የራሱ ምርኮኛ እንዳደረጋቸውና እንዴት እንደሚጫወትባቸው፤
3. የአስመሳዮች እና ደካማ እምነት ያላቸው ሰዎች የሚታዩባቸው ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ፤
4. በአላህ ላይ መመካት ከእምነት ፅንሰ ሀሳቦች አንዱና ኢስላማዊ ግዴታነቱን ጠንካራ ስለ መሆኑ፤
5. ለወንጀለኞችና ከሓዲያን የተዘጋጀው የቀብር ቅጣት የማይቀር ሃቅ ስለመሆኑ፤

6. አላህ ማንንም የማይበድል ፍትሃዊ ጌታ መሆኑን፤
7. ግፈኞችንና በደለኞችን ቅጣት ማከናነብ የአላህ ፍትሃዊነት መገለጫ መሆኑን፤
8. በዚህች ምድር ላይ ካሉ ተንቀሳቃሽ ሕይወት ያላቸው ፍጡራንና በሙሉ እጅግ መጥፎዎቹ በአላህ ላይ የካዱ ካፊሮች ስለ መሆናቸው፤
9. በግፍ የሰጠሙ ታላላቅ ወንጀሎችን ያለገደብ የሚዳፈሩ ወንጀለኞች ወደ ተውበት ንሰሃ የሚያደረጉት ጉዞ መሰናከል የሚበዛበት ስለመሆኑ፤
10. የጠላትን ጦር ማንበርከክ የሚቻለው ጠንካራና የማያዳግም እርምጃ በእነርሱ ላይ በመውሰድ መሆኑን በመገንዘብ ጠንካራ ምትን በካፊሮች ላይ ማሳረፍ ተገቢ እንደሆነ፤
11. የተኩስ አቁም ወይም የሰላም ስምምነት ከተፈረመ በኋላ የጠላት ጦር ቃሉን ለማፍረስ የሚያንገራግር መሆኑ በሚታወቅበት ቅፅበት እርምጃ መውሰድና ቀድሞ ጥቃት መሠንዘር አስፈላጊ መሆኑን፤
12. ጠላትን ለመቋቋም የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶችና ስልጠናዎችን አሟልቶ መገኘት የሙስሊሞች ሁሉ ግዴታ መሆኑን፤
13. ኢስላማዊ ተግባራትን በተገቢው መልኩ የሚፈፅሙ ሙስሊሞች ዘወትር በጠላት ተጠምደው የሚኖሩ መሆናቸውን፤
14. ለጂሃድ ጦርነት ማስፈፀሚያ የሚውሉ ገንዘቦች ሁሉ ለለጋሹ እጥፍ ድርብ ምንዳ እንደሚያስገኙ፤
15. እንደአስፈላጊነቱ ከሓዲያን ጋር የእርቅ ስምምነት ማድረግና የተኩስ አቁም ስምምነት መፈራረም የተፈቀደ መሆኑን፤
16. ሰላምን መፈለግ ሁልጊዜም አስፈላጊ ሲሆን ከጠላት ከመጣ ማስተናገድና ማበረታታት እንደሚገባ፤
17. የግልፅ ውይይት ከፈለጉም ከነሱ ጋር መወያየት እንዳለብን እንማራለን።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ حَسۡبُكَ ٱللَّهُ وَمَنِ ٱتَّبَعَكَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٦٤﴾ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ حَرِّضِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ
عَلَى ٱلۡقِتَالِۚ إِن يَكُن مِّنكُمۡ عِشۡرُونَ صَٰبِرُونَ يَغۡلِبُواْ مِاْئَتَيۡنِۚ وَإِن يَكُن مِّنكُم مِّاْئَةٞ
يَغۡلِبُوٓاْ أَلۡفٗا مِّنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِأَنَّهُمۡ قَوۡمٞ لَّا يَفۡقَهُونَ ﴿٦٥﴾

**64-65.** አንተ ነብይ ሆይ! ለሁሉ ነገር በቂህ አላህ ነው። ለተከተሉህም ምዕምናን (በቂያቸው አላህ ነው)። አንተ ነብይ ሆይ፣ ምዕመናንን ጠላቶቻቸውን በመዋጋት ላይ አደፋፍራቸው። ከናንተ ውስጥ ሃያ ታጋሾች ቢኖሩ ሁለት መቶዎችን ያሸንፋሉ። ከናንተም መካከል መቶ ሰዎች ቢኖሩ ከእነዚያ ከካዱት ሕዝቦች መካከል አንድ ሺሕን ያሸንፋሉ። ምክንያቱም እነርሱ የማያውቁ ህዝቦች ነቻዉና።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (64) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ጋር (39) ሰዎች ሰልመው በአርባኛው ዑመር ሲሰልሙ ይህን አንቀፅ አላህ አወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)። ይህ ታሪክ ደካማ መሆኑ የተነገረለት ነው።

ٱلۡـَٔـٰنَ خَفَّفَ ٱللَّهُ عَنكُمۡ وَعَلِمَ أَنَّ فِيكُمۡ ضَعۡفٗاۚ فَإِن يَكُن مِّنكُم مِّاْئَةٞ صَابِرَةٞ يَغۡلِبُواْ
مِاْئَتَيۡنِۚ وَإِن يَكُن مِّنكُمۡ أَلۡفٞ يَغۡلِبُوٓاْ أَلۡفَيۡنِ بِإِذۡنِ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ مَعَ ٱلصَّـٰبِرِينَ ٦٦

66. አሁን አላህ ከናንተ ላይ አቃለለላችሁ። በእናንተ ውስጥም ድክመት መኖሩን ዐወቀ። ስለዚህ ከናንተ መቶ ታጋሾች ቢኖሩ ሁለት መቶን ያሸንፋሉ። ከናንተ መቶ ሰዎች ቢኖሩ ከነሱ ሁለት መቶን ያሸንፋሉ። አላህ ከታጋሾቹ ጋር ነው።

مَا كَانَ لِنَبِيٍّ أَن يَكُونَ لَهُۥٓ أَسۡرَىٰ حَتَّىٰ يُثۡخِنَ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ تُرِيدُونَ عَرَضَ ٱلدُّنۡيَا وَٱللَّهُ
يُرِيدُ ٱلۡأٓخِرَةَۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ٦٧

67. ለነብይ በምድር ላይ ጠላቶቹን እስኪያደክም ድረስ ለእርሱ ምርኮኞች ሊኖሩት አይገባም። የቅርቢቱን ዓለም ጠፊ ጥቅም ትፈልጋላችሁ። አላህ መጨረሻይቱን ይሻል። አላህ አሸናፊ፣ ጥበበኛ ነው።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (67) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከዑመር ኢብኑል ኸጣብ ሐሳቦች ላይ በአብዛሀኛው የሚስማማ ወህይ ይወርዱ ነበር። ከነዚህም መካከል ነብዩ በበድር ምርኾኞች ላይ ሰዎች አማከረው ነበር። አንዳንዶች «የአጎቶችዎ ልጆች ናቸው። በገንዘብ ይልቀቋቸው» ሲሉ ዑመር ግን «እንግደላቸው» ብለው ስለነበር ይህ የቁርኣን አንቀፅ ወረደና የዑመርን ሐሳብ አፀደቀ። (ሙስሊም፤ ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

لَّوۡلَا كِتَٰبٞ مِّنَ ٱللَّهِ سَبَقَ لَمَسَّكُمۡ فِيمَآ أَخَذۡتُمۡ عَذَابٌ عَظِيمٞ ٦٨
فَكُلُواْ مِمَّا غَنِمۡتُمۡ حَلَٰلٗا طَيِّبٗاۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٦٩

68-69. የአላህ ውሳኔ ባልነበረ ኖሮ በወሰዳችሁት ቤዛ ከባድ ቅጣት በነካችሁ ነበር። (ከጠላት) ከማረካችሁት ሀብት የተፈቀደ መልካም ሲኾን ብሉ። አላህን ፍሩ። አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ قُل لِّمَن فِيٓ أَيۡدِيكُم مِّنَ ٱلۡأَسۡرَىٰٓ إِن يَعۡلَمِ ٱللَّهُ فِي قُلُوبِكُمۡ خَيۡرٗا يُؤۡتِكُمۡ
خَيۡرٗا مِّمَّآ أُخِذَ مِنكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٧٠

70. አንተ ነብይ ሆይ! ከምርኮኞች መካከል በእጃችሁ ላሉት በላቸው አላህ በልቦቻቸው ውስጥ በጎን ነገር እምነትን ቢያውቅ ከተወሰደባችሁ የተሻለን ይሰጣችኋል። ለእናንተም ይምራችኋል። አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና።

በጦርነት ከተማረኩ (70) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዓባስ የተባሉት የነብዩ አጐት «የበድር ቀን ስማረክ ሀያ እፍኝ ወርቅ እኔ ጋር ተገኝቶ ነበር። እና ተወረሰብኝ። ከሰለምኩኝ በኋላ የዚያን ወርቅ ሂሳብ ስጡኝ አልኳቸው። ሃያ አገልጋዮችን ሰጥተውኝ ሁሉም እንዲነግዱልኝ ከማድረጋቸውም

በተጨማሪ በአላህ ዘንድ ከፍተኛ ምንዳ እንደሚጠብቀኝ ተነገረኝ። ይህንን ምክንያት አድርጎ ነበር ይህ የቁርኣን አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَإِن يُرِيدُوا۟ خِيَانَتَكَ فَقَدْ خَانُوا۟ ٱللَّهَ مِن قَبْلُ فَأَمْكَنَ مِنْهُمْ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ﴿٧١﴾

**71.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሊክዱህ ቢፈልጉ ከዚህ በፊት አላህን በእርግጥ ከድተዋል። እናም ከእነርሱ አስመችቶሃል። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነው።

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (64-71) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ሙዕሚኖች መስፈርቱ በተሟላ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማግባባትና ቅስቀሳ ማድረግ አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
2. ከከሃዲ በሚደረገው ትግል ሙስሊሞች አነስተኛ የሆነ ቁጥር ያለው ጦር ቢያሳልፍ እንኳን ማፈግፈግ እንደሌለባቸውና በ (100) ሰዎች የተደራጀ የሙስሊም ጦር 200 ካፊሮችን የመመከትና የመዋጋት ኃላፊነት እንዳለበት፤
3. ለጂሃድ የሚሰለፉ ሰዎችን በተለያዩ ሙያዎች ማሠልጠኑና የጦርና ተያያዥነት ያላቸውን ትምህርቶች መስጠቱ ግዴታ መሆኑን፤
4. በጦርነት ወቅት ትግስትን መላበስ በድፍረትና በፅናት መዋጋት ለድል የሚያበቃ ስለሆነ ያለውን አስፈላጊነት፤
5. አላህ ምንጊዜም በፅናትና በትዕግስት የሚዋጉ የሙስሊምን ኃይል ለመርዳት ዝግጁ እንደሆነና ድልን እንደሚያጎናፅፋቸው፤
6. የሙስሊም መሪዎች በበድር ዘመቻ ወቅት የተማረኩትን የካፊሮች ኃይል ወታደሮች በፊድያ (በገንዘብ ለውጥ) መልቀቃቸው ትክክለኛ እርምጃ እንዳልነበር የሚስታወሱ ቁርአናዊ ግሳፄ፤
7. ምድራዊ ሕይወት ጊዜያዊ መኖሪያ በመሆኗ ለዱንያ መጓጓትና መስገብገብ አስፈላጊ እንዳልሆነና መጨረሻው ዓለም ዘለአለማዊ በመሆኑ ለአኼራ የሚሆን ተግባራትን የሙጥኝ ማለት ያለውን ፋይዳ፤
8. በምርኮ የተገኘን ንብረት መጠቀም የተፈቀደ ስለ መሆኑ፤
9. የነብዩ (ﷺ) አጎት የነበሩ አባስ ታላቅ ክብር የነበራቸው ሶሃባ መሆናቸው፤
10. መልካም ስራዎችን ከሰዎች ደብቆ መስራቱ የሚወደድና ትልቅ ምንዳ የሚያስጥ ስለ መሆኑ፤
11. ማንኛውንም ነገር ለአላህ ብሎ መተው የተሻለ ነገር የሚያስጥ ስለመሆኑ እንማራለን።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَهَاجَرُوا۟ وَجَٰهَدُوا۟ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱلَّذِينَ ءَاوَوا۟
وَّنَصَرُوٓا۟ أُو۟لَٰٓئِكَ بَعْضُهُمْ أَوْلِيَآءُ بَعْضٍ ۚ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَلَمْ يُهَاجِرُوا۟ مَا لَكُم مِّن وَلَٰيَتِهِم
مِّن شَىْءٍ حَتَّىٰ يُهَاجِرُوا۟ ۚ وَإِنِ ٱسْتَنصَرُوكُمْ فِى ٱلدِّينِ فَعَلَيْكُمُ ٱلنَّصْرُ إِلَّا عَلَىٰ قَوْمٍۭ بَيْنَكُمْ
وَبَيْنَهُم مِّيثَٰقٌ ۗ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ بَصِيرٌ ﴿٧٢﴾

**72.** እነዚያ በአላህ ያመኑና ለእሱ ሲሉ ከሀገራቸው የተሰደዱ በአላህ መንገድ ላይ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የታገሉ እና እነዚያም ስደተኞቹን ያስጠጉና የረዱ ሰዎች እነዚያ ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው። እነዚያ ያመኑና

ያልተሰደዱ ሰዎች ደግሞ ለአላህ ብለው እስከሚሰደዱ ድረስ ከእነርሱ ምንም ዝምድና የላችሁም። በሃይማኖት እርዳታን ቢፈልጉባችሁ በእናንተና በእነርሱ መካከል ቃል ኪዳን ባላችሁ ሕዝቦች ላይ ካልሆነ በስተቀር በእናንተ ላይ እነርሱን መርዳት አለባችሁ። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلِيَآءُ بَعۡضٍۚ إِلَّا تَفۡعَلُوهُ تَكُن فِتۡنَةٞ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَفَسَادٞ كَبِيرٞ ﴿٧٣﴾ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَهَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱلَّذِينَ ءَاوَواْ وَّنَصَرُوٓاْ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ حَقّٗاۚ لَّهُم مَّغۡفِرَةٞ وَرِزۡقٞ كَرِيمٞ ﴿٧٤﴾ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنۢ بَعۡدُ وَهَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ مَعَكُمۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ مِنكُمۡۚ وَأُوْلُواْ ٱلۡأَرۡحَامِ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلَىٰ بِبَعۡضٖ فِي كِتَٰبِ ٱللَّهِۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمُۢ ﴿٧٥﴾

73-75. (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ሁሉ ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው። ከምዕምናን ጋር መረዳዳትን ከከሓዲያን መቆራረጥን ባትሠሩት በምድር ላይ ሁከትና ታላቅ ጥፋት ይኾናል። እነዚያ በአላህ ያመኑና ለእሱ ሲሉ የተሰደዱ በአላህ መንገድ ላይ የታገሉ እነዚያም ያስጠጉና የረዱ እውነተኛ አማኞች እነርሱ ናቸው። ለእነርሱም ምሕረትና የከበረ ሲሳይ አለላቸው። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እነዚያ በኋላ ያመኑና ከሀገራቸው የተሰደዱ ከናንተም ጋር ሆነው የታገሉ ከናንተው ናቸው። የዝምድናዎች ባለቤቶች በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው ከከፊሉ (ለመውረስ) የተገቡ ናቸው። “አላህ ሁሉን ነገር ዐዋቂ ነው።

በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ምዕራፍ (75) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በስድስት አይሁዶች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

**በጦርነት ከተማረኩ ገንዘቦች ከአንቀፅ ምዕራፍ (72-75) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በአማኞች መካከል በዕምነታቸውና በመልካም ሥራቸው ልክ መበላለጥ መኖሩን፤
2. ከነብዩ (ﷺ) ጓዶች መካከል አንደኛ ደረጃ የሚሰጣቸው በላጭ ሶሃባዎች አምነው ለኢስላም ሲሉ ከመካ ወደ መዲና ተሰደው የነበሩና በጂሃድ ተሳታፊ የነበሩ ሙሃጂሮችና እነዚህን ስደተኞች የተቀበሉና በጂሃድም የተሳተፉ አንሷሮች መሆናቸውን፤ በመቀጠል
3. ኛ ደረጃ የሚሰጣቸው ከሁደይቢያው ስምምነት በኋላ እምነትን ተቀብለው የተሰደዱና የተዋጉ ሶሃባዎች እንደሆኑ፤ ከነሱ በመቀጠል ደግሞ እምነት ን የተቀበሉ ሆኖም ስደት ያልወጡ ሶሃባዎች መሆናቸውና በደረጃ ቢበላለጡም የነብዩ (ﷺ) ጓዶች ባጠቃላይ የአላህ ቀን አገልጋይ ባሪያዎች እንደነበሩ፤
4. ሙዕሚኖችን መውደድና እነርሱንም በተቻለ መጠን መርዳት ኢስላማዊ ግዴታ ስለመሆኑ፤
5. በጋብቻ በዝምድናና በባርነት የዝምድና ትስስር ከሌለው ሰው ጋር መዋረስ የውርስ ልውውጥ የሚያስፈፅመው የአረቦች ሕግና ሥርዓት የተሻረ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ ከጦርነት የተማረኩ ንብረቶች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (9)
# የንስሓ መግባት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አት ተውበህ)

سُورَةُ التَّوْبَةِ

### የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ (129) ናቸው።
### የሱረቱ አት-ተውባህ መግቢያ

ለምን በስመላህ የለዉም ለሚለው ወሳኝ ጥያቄ ዐሊይ ብን አቢ ጧሊብ በስመለህ ሰላምን ያመለክታል ይህ ምዕራፍ ግን ጦርነት ያወጀ ነው። ስለ ዚህ ነው በበስመላህ ያል ተጀመረው። ብለዋል።

የንስሓ መግባት (የፀፀት) ምዕራፍ ከአገር መከፈት ምዕራፍ በኋላና በቁርአኑ አቀማመጥ መሰረት በዘጠነኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለ በመዲና የወረደ ምዕራፍ ነው።

ምዕራፉ በዘጠነኛው የሒጅራ ዓመት ላይ በአቡበክር ሲዲቅ መሪነት በተፈፀመው የሐጅ ስነ ስርአት ሊፈፀም ተወስኖ መንገድ ከጀመሩ በኋላ ወረደ። አሊይ ቢን አቡ ጧሊብም ይህኑ ምዕራፍ ወደ ሐጅ ይዘው በመሄድ ለሐጃጆች አነበቡላቸው የሚለው በሰፊው ተዘግቧል። ምዕራፉ አላህ ከሙሽሪኮች የተሳሳተ ተግባር የጠራ መሆኑን፤ የተከበሩ የአራት ወራትን ክብር፤ የሙሽሪኮችን ቃል ኪዳን ራሳቸው እስካላፈረሱት ድረስ ማክበር ግዴታ መሆኑንና ካፈረሱ ግን መዋጋቱ ግዴታ መሆኑን ይገልፃል። በማስከተልም ወደ አላህ የመቃረብ ዋና ተልዕኮ በአላህ ማመን መሆኑንና አላህና መልዕክተኛው (ﷺ) ከሁሉ በበለጠ ካልተወደዱ እምነት እንደማይሞላ፤ በራስ ሀይል መመካት ድልን እንደሚያሳጣ፤ የሁነይን ዘመቻ ዕለት የተፈጠረውን ክስተት በማውሳት ሙስሊሞችን ከእንዲህ መሰል ተግባር እንዲታቀቡ ያስጠነቅቃል። ከሐዲ የተባሉ ሰዎች ሁሉ ከዚያ ዓመት በኋላ ወደ መካ መግባት እንደማይችሉ ያውጃል። አይሁድና ነሷራ ግብር እስካልከፈሉ ድረስ እነሱን መዋጋት ተገቢ መሆኑን፤ ለጦርነት ቅስቀሳ ሲደረግ መነሳት እንደሚገባ፤ ከአቅም በላይ ሆኖባቸው ከጂሃድ ስለቀሩ ሰዎች፤ በየጊዜው የፊትና (የፈተና) ቅስቀሳዎችን የሚያደርጉ መናፍቃንን ባህሪ ገልጾ እነርሱንም መዋጋቱ አስፈላጊ መሆኑን በገሀድ ያስተምራል። የንፍቅና በሽታ ያለበት ሰው ሁሉ ቅጣቱ በእሱ ላይ ሶላት አለመስገድ መሆኑን በይፋ ያውጃል። ከጂሃድ ስለሚያስቀሩ ምክንያቶችም ዘርዝሯል።

ምዕራፉ በመቀጠልም ሰዎች ከእምነት አንጻር ያላቸውን ክፍል አውስቶ መናፍቃን ለተንኮል ስለ ሰሩት መስጊድ ታሪክ በአጭሩ ያወሳል። ትክክለኛ አማኞችም እነማን እንደሆኑ ባህሪያቸውን ይዘረዝራል። ከተቡክ ዘመቻ በመቅረታቸው ስለተፀፀት ሰዎችም አላህ ተውበታቸውን መቀበሉን ይገልፃል። አላህ ነብዩን (ﷺ) መረጠ ሲል ሰዎችን ለማድከም ፈልጎ እንዳልሆነ፤ ነብዩ (ﷺ) ራሳቸው አዛኝና ሩህሩህ እንደሆኑ በመግለጽ መልዕክቱን ያጠቃልላል። ይህ ምዕራፍ እንደሌሎቹ የመዲና ምዕራፎች ሁሉ ከዐቂዳ ይልቅ በኢስላማዊ ሕጎች ላይ ትኩረት ይሰጣል።

ምዕራፉ የወረደው ከላይ እንዳልኩት የመካ አስተዳደር በሙስሊሞች እጅ ከገባ በኋላ በ (9) ኛው ዓመት ላይ ነብዩ (ﷺ) ከተቡክ ዘመቻ ሲመለሱ ስለነበረ አብዛኛው የምዕራፉ አናቅፅ በዚህ ዘመቻ ዙሪያ ያተኮራሉ። ብዙሃኑ ዓሊሞች ምዕራፉ እንደ "የእንስሳዎች ምዕራፍ" በአንድ ጊዜ የወረደው ስለመሆኑ ተስማምተውበታል።

ስለዚህ ይህ ምዕራፍ በዘጠነኛው አመት ላይ አቡበክር ይዘውት ወደ መካ ለሄዱት ህዝብ በዙል ሂጃ ወር አስረኛ ቀን ላይ ዐሊይ ቢን አቡ ጧሊብ በንባብ ያሰሙት ምዕራፍ ነው። ይህ አባባልና ሌሎችን መሰል አናቅፅን ለማጣጣም ብዙ ተብለዋል። ይህ አንቀፅ የሰይፉ አንቀፅ በመባል ይታወቃል። ስለ እሱም አስተምህሮት ብዙ ተብሏል። አንዳንድ ዐሊሞች በየትኛውም ሰአትና ቦታ ላይ መተግበር አለባት ይላሉ። ከመቶ ሃያ አራት ያላነሱ የቁርኣን አናቅፅን ሽሯልም ተብሏል።

بَرَآءَةٞ مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦٓ إِلَى ٱلَّذِينَ عَٰهَدتُّم مِّنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ١ فَسِيحُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ أَرۡبَعَةَ
أَشۡهُرٖ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّكُمۡ غَيۡرُ مُعۡجِزِي ٱللَّهِ وَأَنَّ ٱللَّهَ مُخۡزِي ٱلۡكَٰفِرِينَ ٢

**1-2.** (ይህ) ከአላህና ከመልዕክተኛው ወደ እነዚያ ቃል ኪዳን ወደ ተጋባችኋቸው አጋሪዎች የሚደርስ የውል መሻሪያ መልዕክት ነው። (ከሓዲያን ሆይ!) በምድር ላይ አራት ወሮችን ጸጥተኞች ስትሆኑ ተንቀሳቀሱ። እናንተ ከአላህ ቅጣት የማታመልጡ መሆናችሁንና አላህ ከሓዲያንን አዋራጅ መሆኑን እወቁ።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከተቡክ ዘመቻ ሲመለሱና ሐጅ ማድረግ ሲፈልጉ ጣኦት አምላኪዎች በድሮው ስርዓታቸው እንደሚመጡ ሲያስታውሱ አቡበክር እንዲመሩት አዘዙ። በዚሁ ሐጅ ላይ የዚህን መጀመሪያ አናቅፅ በማንበብ ለሕዝቡ ማስጠንቀቂያ እንዲያደርጉት ሆነ። ከዚያም የዓሊይ መላክ ተከሰተ።

وَأَذَٰنٞ مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦٓ إِلَى ٱلنَّاسِ يَوۡمَ ٱلۡحَجِّ ٱلۡأَكۡبَرِ أَنَّ ٱللَّهَ بَرِيٓءٞ مِّنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ وَرَسُولُهُۥۚ
فَإِن تُبۡتُمۡ فَهُوَ خَيۡرٞ لَّكُمۡۖ وَإِن تَوَلَّيۡتُمۡ فَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّكُمۡ غَيۡرُ مُعۡجِزِي ٱللَّهِۗ وَبَشِّرِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ
بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ٣ إِلَّا ٱلَّذِينَ عَٰهَدتُّم مِّنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ثُمَّ لَمۡ يَنقُصُوكُمۡ شَيۡـٔٗا وَلَمۡ يُظَٰهِرُواْ عَلَيۡكُمۡ
أَحَدٗا فَأَتِمُّوٓاْ إِلَيۡهِمۡ عَهۡدَهُمۡ إِلَىٰ مُدَّتِهِمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُتَّقِينَ ٤ فَإِذَا ٱنسَلَخَ ٱلۡأَشۡهُرُ ٱلۡحُرُمُ
فَٱقۡتُلُواْ ٱلۡمُشۡرِكِينَ حَيۡثُ وَجَدتُّمُوهُمۡ وَخُذُوهُمۡ وَٱحۡصُرُوهُمۡ وَٱقۡعُدُواْ لَهُمۡ كُلَّ مَرۡصَدٖۚ فَإِن تَابُواْ
وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَوُاْ ٱلزَّكَوٰةَ فَخَلُّواْ سَبِيلَهُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٥

**3-5.** (ይህ) ከአላህና ከመልዕክተኛው በታላቁ ሐጅ ቀን የወጣ አላህ እና መልዕክተኛው ከአጋሪዎቹ ንፁህ ነው የሚል አዋጅ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከክህደት ብትፀፀቱ ግን እርሱ ለእናንተ በላጭ ነው። ከእምነት ብትሸሹም እናንተ አላህን የማታቅቱት መሆናችሁን እወቁ በማለት ወደ ሰዎች የሚደርስ ማስታወቂያ ነው። እነዚያን በአላህ የካዱትን ሰዎች በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው። እነዚያ*[1] ከአጋሪዎቹ መካከል እነዚያ ቃል ኪዳን የተጋባችሁላቸውና ከዚያ ምንም ያላጎደሉባችሁ በእናንተ ላይ ለማጥቃት አንድንም ያልተባበሩባችሁ ቃል ኪዳናቸውን እስከ ጊዜያቸው መጨረሻ ሙሉላቸው።*[2] አላህ ጥንቁቆችን ይወዳልና። የተከበሩት ወሮች ባለቁ ጊዜ አጋሪዎቹን ባገኛችሁባቸው ስፍራ ሁሉ ግደሏቸው። ያዟቸውም። ከበቧቸውም። እነርሱንም ለመጠባበቅ ስትሉ በየኬላው ላይ ተቀመጡ። ሆኖም ቢፀፀቱ፣ ሶላትን በደንቡ ቢሰግዱና ግዴታ የሆነባቸውን የዘካ ምጽዋትን በትክክል ከሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው። አላህ መሀሪና አዛኝ*[3] ነውና።

✶1 «እነዚያ . ሲቀሩ» የተባሉት ክፍሎች ማንነትን በተመለከተ በተፍሲር ምሁራን ዘንድ ቁረይሾች ወይም በኒ በክሮች ሊሆኑ ይችላሉ ተብሏል።

✶2 በቃላቸው የሞሉ በኒኹዘይማ፤ በኒ ሙድሊጅ፤ በኒ ሙደርህ የተባሉት ናቸው።

✶3 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) ካለፉ በኋላ አቡበክር ኸሊፋ ሲሆኑ፤ ከዐረቦች መካከል በአላህ ያመነው ሁሉ አላህን ካደ፤ ዑመርም «አቡበክር ሆይ! የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ሰዎች ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም እስኪሉ ድረስ እጋደላቸው ዘንድ ታዝዣለሁ። ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም ያለ ሰው ንብረቱንና ሕይወቱን ከኔ ጠብቋል። ሌላው መተሳሰቡ ግን በአላህ ላይ ነው» አሉ። ዑመርም «ሰዎችን እንዴት ትጋደላለህ?» ሲሉ ጠየቋቸው። አቡበክርም «በአላህ እምላለሁ!» በሶላትና በዘካ መካከል ልዩነትን የፈጠረን ሁሉ እዋጋዋለሁ። በእርግጥ ዘካ ገንዘባዊ ግዴታ ነው። በአላህ እምላለሁ ለአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ይሰጡት የነበረውን የግመል ማሰሪያ ገመድ እንኳን ቢከለክሉኝ እሷን በመከልከላቸው እጋደላቸዋለሁ»አሉ። ዑመርም «በአላህ እምላለሁ! በእርግጥ አላህ የአቡበክርን ልቦና ለመጋደል እንዳሰፋ ከመመልከት በስተቀር ሌላ ነገር አላየሁም። እኔም እሳቸው የወሰኑት ውሳኔ ትክክል መሆኑን አረጋገጥኩ» ሲሉ ተናሩ።

وَإِنۡ أَحَدٞ مِّنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ٱسۡتَجَارَكَ فَأَجِرۡهُ حَتَّىٰ يَسۡمَعَ كَلَٰمَ ٱللَّهِ ثُمَّ أَبۡلِغۡهُ مَأۡمَنَهُۥۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ قَوۡمٞ لَّا يَعۡلَمُونَ ٦ كَيۡفَ يَكُونُ لِلۡمُشۡرِكِينَ عَهۡدٌ عِندَ ٱللَّهِ وَعِندَ رَسُولِهِۦٓ إِلَّا ٱلَّذِينَ عَٰهَدتُّمۡ عِندَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِۖ فَمَا ٱسۡتَقَٰمُواْ لَكُمۡ فَٱسۡتَقِيمُواْ لَهُمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُتَّقِينَ ٧ كَيۡفَ وَإِن يَظۡهَرُواْ عَلَيۡكُمۡ لَا يَرۡقُبُواْ فِيكُمۡ إِلّٗا وَلَا ذِمَّةٗۚ يُرۡضُونَكُم بِأَفۡوَٰهِهِمۡ وَتَأۡبَىٰ قُلُوبُهُمۡ وَأَكۡثَرُهُمۡ فَٰسِقُونَ ٨

**6-8.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአጋሪዎች መካከል አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅህ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው። ከዚያ ወደ ሰላም ማግኛው ስፍራ አድርሰው። ይህም የሆነው እነርሱ የማያውቁ ህዝቦች በመሆናቸው ነው። ለአጋሪዎች ከአላህና ከመልዕክተኛው ዘንድ የሰላም ቃል ኪዳን እንዴት ይኖራቸዋል? እነዚያ በተከበረው መስጊድ ዘንድ ቃል ኪዳን የገባችሁላቸው ሰዎች ብቻ ሲቀሩ። እነዚያማ በቃል ኪዳናቸው ለእናንተ ቀጥ እስካሉላችሁ ድረስ በቃላችሁ ቀጥ በሉላቸው። አላህ በሁሉ ነገር ጥንቁቆችን ይወዳልና። በእናንተ ላይ ቢያይሉ በእናንተ ውስጥ ዝምድናንና ቃልኪዳንን የማይጠብቁ ሰዎች ሲሆኑ እንዴት ከአላህና ከመልዕክተኛው ዘንድ ቃልኪዳን ይኖራቸዋል? በአፎቻቸው ይሸነግሏችኋል። ልቦቻቸው ግን እምቢ ይላሉ። አብዛኞቻቸውም አመፀኞች ናቸው።

ٱشۡتَرَوۡاْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ ثَمَنٗا قَلِيلٗا فَصَدُّواْ عَن سَبِيلِهِۦٓۚ إِنَّهُمۡ سَآءَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٩
لَا يَرۡقُبُونَ فِي مُؤۡمِنٍ إِلّٗا وَلَا ذِمَّةٗۚ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُعۡتَدُونَ ١٠ فَإِن تَابُواْ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ
وَءَاتَوُاْ ٱلزَّكَوٰةَ فَإِخۡوَٰنُكُمۡ فِي ٱلدِّينِۗ وَنُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ١١

**9-11.** በአላህ አንቀፆች ጥቂትን ዋጋ ገዙ። እናም ከመንገዱም ከራሳቸው አልፎ ሌሎችን ሰዎች ከኢስላም አገዱ። እነርሱ ይሰሩት የነበሩት ሥራም እጅግ በጣም ከፋ። ምእመናን ዝምድናንም ሆነ ቃል ኪዳንን አይጠብቁም። ወሰን አላፊዎች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። (ሙስሊሞች ሆይ!) ቢፀፀቱ[*1]፤ ሶላትንም ደንቡን አሟልተው ቢሰገዱና ግድ የሆነባቸውንም ዘካን በትክክል ቢሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው[*2]። ለሚያውቁ ህዝቦች ሁሉ አንቀፆችን እናብራራለን።

✶1 ኢብኑ ዘይድ፡- አላህ ሶላትና ዘካን በአንድ ደነገገ። በመሐላቸውም በምንም አልለየም። ሶላትን ያለዘካ በምንም መልኩ አይቀበልም። አቡበክር አላህ ይማራቸው «በጌታዬ ይሁንብኝ በነብዩ ጊዜ ይከፍሉት ከነበረው አንዲት ገመድ እንኳን ቢከለክሉኝ ጦርነት አውጅባቸዋለሁ»። ምን ያህል ቢረዱ ነው እንዲህ ያሉ፤ ኢብኑ መስዑድ፡- በሶላትና በዘካ ታዛችኋል። ዘካ ያልሰጠ ሶላቱ ተቀባይነት የለውም።

✶2 ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብ ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ኢስላም ከአምስት መሰረቶች ላይ ተንፏል። እነርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተና መሆናቸውን መመስከር ሶላትን በወቅቱ መስገድ፤ ዘካን መስጠት፤ ሐጅጅ ማድረግና ረመዷንን መፆም ናቸው።

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ቡረይደት እንዳስተላለፉት ነብዩ እንዲህ ብለዋል፡- «በኛና በነርሱ በአስመሳዮች መካከል ያለው ቃል ኪዳን ሶላት ነው እርሷን የተዋት በእርግጥ ካደ» ቲርሚዞ በዘገቡት ሐዲስ ሽቂቅ ብኑ ዐብደላህ የተባት ታላቅ ታቢዒይ እንዲህ ብለዋል፡- «የነብዩ ባልደረቦች ከስራዎቹ መካከል አለመፈፀሙን እንደ ክህደት የሚያዩት ተግባር ሶላት ብቻ ነበር»

وَإِن نَّكَثُوٓاْ أَيۡمَٰنَهُم مِّنۢ بَعۡدِ عَهۡدِهِمۡ وَطَعَنُواْ فِي دِينِكُمۡ فَقَٰتِلُوٓاْ أَئِمَّةَ ٱلۡكُفۡرِ إِنَّهُمۡ
لَآ أَيۡمَٰنَ لَهُمۡ لَعَلَّهُمۡ يَنتَهُونَ ١٢ أَلَا تُقَٰتِلُونَ قَوۡمٗا نَّكَثُوٓاْ أَيۡمَٰنَهُمۡ وَهَمُّواْ بِإِخۡرَاجِ ٱلرَّسُولِ
وَهُم بَدَءُوكُمۡ أَوَّلَ مَرَّةٍۚ أَتَخۡشَوۡنَهُمۡۚ فَٱللَّهُ أَحَقُّ أَن تَخۡشَوۡهُ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَ ١٣ قَٰتِلُوهُمۡ
يُعَذِّبۡهُمُ ٱللَّهُ بِأَيۡدِيكُمۡ وَيُخۡزِهِمۡ وَيَنصُرۡكُمۡ عَلَيۡهِمۡ وَيَشۡفِ صُدُورَ قَوۡمٖ مُّؤۡمِنِينَ ١٤
وَيُذۡهِبۡ غَيۡظَ قُلُوبِهِمۡۗ وَيَتُوبُ ٱللَّهُ عَلَىٰ مَن يَشَآءُۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ١٥

**12-15.** ከቃልኪዳናቸው በኋላ መሀላዎቻቸውን ካፈረሱና ሃይማኖታችሁን ካንቋሸሹ የክህደት መሪዎች ከክህደት ተግባራቸው ይከለከሉ ዘንድ ተዋጓቸው። እነርሱ ምንም ቃልኪዳን የላቸውምና። እነዚያ መሀላዎቻቸውን ያፈረሱትን፤

መልዕክተኛውንም ከሀገር ለማውጣት ያሰቡትንና እነርሱ ለመጀመሪያ ጊዜ ጦርነት የጀመሯችሁን ህዝቦች አትዋጓቸውምን? ትፈሯቸዋላችሁን? ትክክለኛ አማኞች ከሆናችሁ አላህን ይበልጥ ልትፈሩት የተገባው ነው። (ሙስሊሞች ሆይ!) ተጋደሏቸው። አላህ በእጃችሁ ያሰቃያቸዋል። ያዋርዳቸዋልም። በእነርሱም ላይ ይረዳችኋል። የአማኝ ህዝቦችን ልቦችም ያሽራል። የልቦቻቸውንም ቁጭት ያስወግዳል። አላህ ከሚፈልገው ሰው ላይ ፀፀትን ይቀበላል። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (12) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ቃላቸውን በማፍረስ ነብዩን (ﷺ) ከአገር ለማባረር ባሠቡት የመካ መሪዎች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ዋሒዲ)

ከንሰሓ መግባት (14) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የነብዩ (ﷺ) ወዳጆች የነበሩ በኒ ኹዛአዎች የመኮች ወዳጆች የነበሩትን በኒ በክሮችን በተዋጉበት አጋጣሚ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሙስሊም፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

**ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-12) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ለኢስላምና ለሙስሊሞች ጠቀሜታ ያለው ከሆነና ለሙስሊሙ ህብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ፋይዳ ካለው ከከሓዲያን ኃይል ጋር የስምምነት ውል መፈፀም የተፈቀደ ስለመሆኑ፤
2. የአላህን ፍራቻ የሰነቁ፤ የአላህ ቅን አገልጋይ ባሪያዎች ያላቸው ክብርና ማዕረግ ምን እንደሆነ፤
3. ከሙስሊሞች በኩል ለከሓዲያን በየትኛውም ሀይል ቢሆን ከአላህ የተሰጠ ማስጠንቀቂያ፤
4. ለካፊሮች ቃል ኪዳን መግባት እንደሚቻል፤
5. የነብዩ (ﷺ) ትዕዛዝ ልክ እንደ አላህ ትእዛዝ መታየቱን፤
6. ቃልን ማክበር በኢስላም እጅግ የተወደደ ተግባር ስለመሆኑ፤
7. በጦርነት ጊዜ ቁርጠኛ መሆንና በጠላት ላይ ብርቱ ኃይልን ማሳረፍ ያለውን አስፈላጊነት፤
8. የአረብን ሀገራት ከክህደትና ከማጋራት እንዲሁም እነዚህን ወንጀሎች ከሚያሰራጩ ወንጀለኞች ማፅዳት ኢስላማዊ ኃላፊነት እንደሆነ፤
9. ሰላት መስገድ እምነትን ለመሙላት የሚያስችልና ከኢስላማዊ ዋና የሃይማኖቱ ማዕዘናት ዋናው ተግባር ስለ መሆኑ፤
10. የጉርብትናን ሐቅ መሙላት በአላህ ዘንድ ምንዳ እንዳለውና ኢስላማዊ ግዴታ እንደሆነ፤
11. የኢስላምን ሃይማኖት ለመማርና ውስጡን ለማወቅ በመፈለግ ወደ ሙስሊም ሀገራት ለመግባት ፈቃድ እንዲሰጠው የጠየቀ ከሃዲ ወደ ሙስሊም ሀገራት እንዲገባ የሚፈቀድለት ስለ መሆኑ፤
12. ከሓዲያን ለማስተማር ሲባል የቁርአን ትርጉምም ሆነ የቁርአን ንባብ በእጃቸው ቢነኩት እንደሚፈቀድ፤
13. የቁርአን ትርጉምም ሆነ የቁርአን ንባብ የሚፃፍባቸው ፊደላት የአላህ ንግግሮችና ቃላት ስለ መሆናቸው፤
14. የአላህን ኃያልነትና ጌትነት እንዲሁም ብቸኛ አምላክነት በመገንዘብ ዘወትር የእርሱን ትዕዛዝ መጠባበቅና ለዝምድና ሀቅ ትኩረት ሰጥቶ መጠባበቅ ግዴታ መሆኑን፤

15. ካፊሮችን በተፈጥሯዊ ስብእናቸው ሳይሆን በሚያሳዩዋቸው የኩፍር ተግባራት የተነሳ ማውገዝና መጥፎነታቸውን ማረጋገጥ ተገቢ መሆኑን፤
16. ሰዎችን መበደልን እለታዊ ተግባሩ አድርጎ የሚንቀሳቀስ ግፈኛ በምንም ዓይነት አመኔታ ሊጣልበት እንደማይገባ፤
17. ተውሒድ፤ ሠላት፤ ዛካ የኢስላም ሃይማኖት ህልውና የቆመባቸው ፅንሰ ሀሳቦችና ተግባራዊ መገለጫዎች መሆናቸውን፤
18. የሃይማኖትን ድንጋጌዎችና ቁርኣንን ማጣጣልና የኢስላምን ሃይማኖት መዝለፍ ከሃይማኖቱ የሚያወጣ ወንጀል መሆኑን እንማራለን።

أَمۡ حَسِبۡتُمۡ أَن تُتۡرَكُواْ وَلَمَّا يَعۡلَمِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ جَٰهَدُواْ مِنكُمۡ وَلَمۡ يَتَّخِذُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ
وَلَا رَسُولِهِۦ وَلَا ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَلِيجَةٗۚ وَٱللَّهُ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ﴿١٦﴾

**16.** (መናፍቃን ሆይ)፣ አላህ ከመካከላችሁ ማን በትክክል ለአላህ ምስዋዕት የሚከፍሉትንና (የታገሉትንና) ከአላህ፤ ከመልዕክተኛውና ከትክክለኛ አማኞች በስተቀር አማካሪ ያልያዙትን ክፍሎች ለይቶ ሳያውቅ (ሳይገልጽ) የምትተዉ መሰላችሁን። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ዉስጡን ያውቃል።

مَا كَانَ لِلۡمُشۡرِكِينَ أَن يَعۡمُرُواْ مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ شَٰهِدِينَ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِم بِٱلۡكُفۡرِۚ أُوْلَٰٓئِكَ حَبِطَتۡ
أَعۡمَٰلُهُمۡ وَفِي ٱلنَّارِ هُمۡ خَٰلِدُونَ ﴿١٧﴾ إِنَّمَا يَعۡمُرُ مَسَٰجِدَ ٱللَّهِ مَنۡ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ
ٱلۡأٓخِرِ وَأَقَامَ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَى ٱلزَّكَوٰةَ وَلَمۡ يَخۡشَ إِلَّا ٱللَّهَۖ فَعَسَىٰٓ أُوْلَٰٓئِكَ أَن يَكُونُواْ مِنَ
ٱلۡمُهۡتَدِينَ ﴿١٨﴾ ۞ أَجَعَلۡتُمۡ سِقَايَةَ ٱلۡحَآجِّ وَعِمَارَةَ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ كَمَنۡ ءَامَنَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ
ٱلۡأٓخِرِ وَجَٰهَدَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِۚ لَا يَسۡتَوُۥنَ عِندَ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٩﴾

**17-19.** አጋሪዎች በራሳቸው ላይ በክህደት የሚመሰክሩ ሲሆኑ የአላህን መስጊዶች ሊንከባከቡ አይገባቸውም። እነዚያ ሥራዎቻቸው የተበላሹና በአኼራም በእሳት ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። የአላህን መስጊዶች የሚሰሩ ሰዎች በአላህና በመጨረሻው ቀን ያመኑ፣ ሶላትንም ደንቡን ጠብቀው የሚሰግዱ፣ ግዴታ ምጽዋትን በትክክል የሚሰጡ፤ ከአላህ ሌላ (ምንንም) ያልፈሩ ሰዎች ብቻ ናቸው። እንዲህ ያሉት ሰዎች ቀናዉን መስመር ከያዙት ሊሆኑ ተረጋገጠ። ሰዎችን ማጠጣትንና የተከበረውን መስጊድ መንከባከብን፤ በአላህና በመጨረሻው ቀን እንዳመነና በአላህ መንገድ እንደታገለ ሰው እምነትና ትግል አደረጋችሁን? በአላህ ዘንድ ፈፅሞ ሁለቱ ተግባሮች አይስተካከሉም። አላህ በዳይ ህዝቦችን ሁሉ ወደ ቀጥተኛው መንገድ አይመራምና።

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ ከ (17-19) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የነብዩ (ﷺ) አጎት የሆኑት ዐባስ ቢን ዐብዱል ሙጦሊብ የበድር ቀን ተማርከው ሳለ ሙስሊሞች በየ አጋጣሚው በክህደቱና ዝምድናን ባለ ማክበሩ እየወቀሱትና አስቸግሩት። ዐባስም «ሁል ጊዜ ደካማ ጎናችንን ብቻ ነው የምታነሱት። አንድም ቀን ጠንካራ ጎናችን ስታወሱ አልሰማም» በማለት መልስ ሰጡ። በዚህ ጊዜ «ዐሊይ ለመሆኑ ጠንካራ ጎን አላችሁን?» አላቸው። አዎ እንዴት የለንም? እኛ አይደለን መስጊድን የሰራን? ካዕባን ያለበስን? ሁጃጆችን የምናጠጣ ለችግረኞች የምንረዳ አይደለንምን?» በማለታቸው እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። (ቁርጡቢ፤ ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَهَاجَرُواْ وَجَٰهَدُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ أَعْظَمُ دَرَجَةً عِندَ ٱللَّهِۚ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْفَآئِزُونَ ﴿٢٠﴾ يُبَشِّرُهُمْ رَبُّهُم بِرَحْمَةٍ مِّنْهُ وَرِضْوَٰنٍ وَجَنَّٰتٍ لَّهُمْ فِيهَا نَعِيمٌ مُّقِيمٌ ﴿٢١﴾ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًاۚ إِنَّ ٱللَّهَ عِندَهُۥٓ أَجْرٌ عَظِيمٌ ﴿٢٢﴾

**20-22.** እነዚያ በአላህ ያመኑት ከየአገሮቻቸውም የተሰደዱት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው። እነዚያም እነርሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ማለትም እነርሱ ብቻ ናቸው።✶ ጌታቸው ከእርሱ በሆነው እዝነትና ውዴታ፣ በውስጧ የማያቋርጥ መጠቀሚያ ባለባት ገነትም ያበስራቸዋል። በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ (ያበስራቸዋል)። አላህ እርሱ ዘንድ ታላቅ ምንዳ አለና።

✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-

(ሀ) «በአላህና በመልዕክተኛው ያመነ፤ አምስት አውቃት ሶላቱን የሰገደ፤ የረመዳንን ፆም የፆመ በአላህ መንገድ ላይ ትግል ባያደርግና እንዲሁም በተወለደበት ምድር እንዲያው ቢቀመጥም አላህ ጀነት እንዲያስገበው የማድረግ መብት አለው። ሶሐቦችም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሰዎችን በዚህ እናብስራቸውን?» ሲሉ ጠየቋቸው። እሳቸውም «በጀነት ውስጥ አንድ መቶ ደረጃዎች አሉ። እነዚህን ደረጃዎች በአላህ መንገድ ላይ ለሚጋደሉ ሰዎች አላህ አዘጋጅቶላቸዋል። በሁለቱ ደረጃዎች መካከል ያለው ልዩነት ልክ በሰማይና በምድር መካከል ያለውን ርቀት የሚያህል ነው። አላህን ከጠየቃችሁ«ፊርደውስን» ጠይቁት። በእርግጥ «ፊርደወስ» የጀነት በላጬና ከፍተኛው ደረጃ ነው» ሌላ የሐዲሱ አስተላለፊ ሶሓብይ ከሐዲሱ ላይ የሚከተለውን አክለዋል። «የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል ብዬ አስባለሁ «ከፊርደወስ በላይ እጅግ በጣም ሩህሩህ የሆነው የአላህ ዙፋን አለ። ከስሩም የጀነት ወንዞች ይፈልቃሉ»

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ፤ ከምእመናን መካከል ነፍሶቻቸው ከእኔ ኋላ መሆንን የማትወድ ሰዎች ባይኖሩ፤ እንዲሁም እነሱ የማይጓዙበትን ነገር የማላገኝ ብሆን ኖሮ በአላህ መንገድ ላይ ከሚደረጉ የጦር ትግሎች ከመሳተፍ ወደ ኋላ አልልም ነበር። ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ፤ በእርግጥ በአላህ መንገድ ላይ ከሞትኩ ዳግም ሕያው መሆንን፤ አሁንም እየሞትኩ ዳግም ሕያው መሆንን በወደድኩ ነበር»

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُوٓاْ ءَابَآءَكُمۡ وَإِخۡوَٰنَكُمۡ أَوۡلِيَآءَ إِنِ ٱسۡتَحَبُّواْ ٱلۡكُفۡرَ
عَلَى ٱلۡإِيمَٰنِۚ وَمَن يَتَوَلَّهُم مِّنكُمۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٢٣ قُلۡ إِن كَانَ ءَابَآؤُكُمۡ
وَأَبۡنَآؤُكُمۡ وَإِخۡوَٰنُكُمۡ وَأَزۡوَٰجُكُمۡ وَعَشِيرَتُكُمۡ وَأَمۡوَٰلٌ ٱقۡتَرَفۡتُمُوهَا وَتِجَٰرَةٞ تَخۡشَوۡنَ
كَسَادَهَا وَمَسَٰكِنُ تَرۡضَوۡنَهَآ أَحَبَّ إِلَيۡكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَجِهَادٖ فِي سَبِيلِهِۦ
فَتَرَبَّصُواْ حَتَّىٰ يَأۡتِيَ ٱللَّهُ بِأَمۡرِهِۦۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ٢٤

**23-24.** እናንተ በትክክል በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፤ አባቶቻችሁንና ወንድሞቻችሁን ክህደትን ከእምነት አብልጠው ከወደዱ ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዟቸው። ከናንተ መካከል እነርሱን ወዳጅ የሚያደርጓቸው ሁሉ በዳዮች ማለት እነዚያ እነርሱ ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አባቶቻችሁና፤ ወንዶች ልጆቻችሁም፤ ወንድሞቻችሁም፤ ሚስቶቻችሁም ዘመዶቻችሁም፤ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶችም፤ መክሰሯን የምትፈሯት ንግድና የምትወዷቸው መኖሪያዎችም በእናንተ ዘንድ ከአላህ፤ ከመልዕክተኛውና በእርሱ መንገድ ከመታገል* ይበልጥ የተወደዱ ከሆኑ አላህ ቅጣቱን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው። አላህ አመፀኞች ህዝቦችን አይመራም።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከ (23-24) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡-
ስደት በታዘዘ ጊዜ ለቤተሠባቸውና ለንብረታቸው ሲሉ ስደትን ባልተሠደዱ ሙስሊሞች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደ። (ዋሒዲ እና ኢብኑ ልጀውዚ)

* ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ መስዑድ እንዲህ ሲሉ አስተላፈፈዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከስራዎች ሁሉ በላጩ የትኛው ነው?» በማለት ጠየቅኳቸው። «ሶላትን ወቅቱን ጠብቆ መስገድ» ሲሉ መለሱ። «ከርሱ ቀጥሎስ?» አልኳቸው። «ለወላጆች በጎ መዋል» አሉ። «ከርሱ ቀጥሎስ?» አልኳቸው። «በአላህ መንገድ መታገል» አሉ። ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ዘር እንዲህ ሲሉ አስተላፈዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከስራዎች ሁሉ በላጩ የትኛው ነው?» በማለት ጠየቅኳቸው። «በአላህ ማመንና በርሱ መንገድ መታል» ነው ሲሉ መለሱልኝ።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዲህ ሲሉ አስተላፈዋል፡- አጎቴ አነስ ኢብኑ ነድር በበድር ጦርነት አልተሳተፈም ነበርና። መልዕክተኛውን፡- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከአጋሪዎች ጋር ባደረጉት የመጀመሪያው ጦርነት ላይ አልተሳተፍኩም። አላህ ከአጋሪዎች ጋር በሚደረግ ውጊያ ካሳተፈኝ የማደርገውን ያያል» አለ። የኡሑድ ጦርነት ዕለት ሙስሊሞች ለጥቃት በተጋለጡ ጊዜ «አላህ ሆይ! ባልደረቦቼ ለፈፀሙት ጥፋት ይቅርታ እጠይቅሃለሁ። አጋሪዎች ከፈፀሙት ጥፋትም ራሴን አፀዳለሁ«አለና ወደ ፊት ገሰገሰ፤ ሰዕድ ኢብኑ ሙዓዝን አገኘው። «ሰዕድ ሆይ!ጀነት ናፍቃኛለች። በነድር አምላክ እምላለሁ! ከኡሑድ በስተጀርባ መልካም ሽታዋ ያውደኛል»አለ። ሰዕድም፡- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርሱ የፈፀመውን ጀብዱ መፈፀም አልሆነልኝም» አለ።

አነስ እንዳሉት ከአካሉ ላይ ከሰማንያ በላይ ከሆነ ቦታ በሰይፍ ተሸርክቶ፤ በጦር ተወግቶና በቀስት ቆስሎ አገኘነው። ከመካከላችን ያወቀው አልነበረም። እህቱ በጣቶቹ ለየችው። ተከታዩ የቁርኣን አንቀፅ የወረደው ለርሱና ለመሰሎቹ እንደሆነ እናምን ነበር፡- «ከአማኞች መከካል ለአላህ የገቡትን ቃል....» (33:23)

لَقَدۡ نَصَرَكُمُ ٱللَّهُ فِي مَوَاطِنَ كَثِيرَةٖ وَيَوۡمَ حُنَيۡنٍ إِذۡ أَعۡجَبَتۡكُمۡ كَثۡرَتُكُمۡ
فَلَمۡ تُغۡنِ عَنكُمۡ شَيۡـٔٗا وَضَاقَتۡ عَلَيۡكُمُ ٱلۡأَرۡضُ بِمَا رَحُبَتۡ ثُمَّ وَلَّيۡتُم مُّدۡبِرِينَ ٢٥
ثُمَّ أَنزَلَ ٱللَّهُ سَكِينَتَهُۥ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ وَعَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَأَنزَلَ جُنُودٗا لَّمۡ تَرَوۡهَا وَعَذَّبَ
ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۚ وَذَٰلِكَ جَزَآءُ ٱلۡكَٰفِرِينَ ٢٦ ثُمَّ يَتُوبُ ٱللَّهُ مِنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ عَلَىٰ مَن يَشَآءُۗ
وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٢٧

**25-27.** (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህ በብዙ የጦር ሜዳዎች ላይ እገዛውን ለግሶላችኋል። የሁነይን ቀን ብዛታችሁ ባስደነቀቻችሁና ለእናንተም ብዛት ምንም ባልጠቀመቻችሁ ጊዜ ምድርም ከስፋቷ ጋር በጠበበቻችሁና ከዚያ ተሸናፊዎች ሆናችሁ በዞራችሁ ጊዜ ረዳችሁ። ከዚያ አላህ እርጋታውን በመልዕክተኛውና በምዕመናኖች ላይ አወረደ። ያላያችኋቸውን ሰራዊት አወረደ። እነዚያን በአላህ የካዱትንም ሰዎች በመግደልና በመማረክ አሰቃየ። ይህም የከሓዲያን ምንዳ ነው። ከዚያ ከዚህ በኋላ አላህ ከሚፈልገው ሰው ላይ ፀፀትን ይቀበላል። አላህ እጅግ መህሪ፤ አዛኝ ነውና።

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ (25) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የሁነይን ዘመቻ እለት ነብዩ (ﷺ) ባልደረቦቻቸውን ሲመክሩና አላህን እንዲፈሩ ሲያስታውሱ አንድ ሠው ተነስቶ «ዛሬ ቁጥራችን በማነሱ አንሸነፍም» በማለቱ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّمَا ٱلۡمُشۡرِكُونَ نَجَسٞ فَلَا يَقۡرَبُواْ ٱلۡمَسۡجِدَ ٱلۡحَرَامَ بَعۡدَ عَامِهِمۡ هَٰذَاۚ
وَإِنۡ خِفۡتُمۡ عَيۡلَةٗ فَسَوۡفَ يُغۡنِيكُمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦٓ إِن شَآءَۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ٢٨

**28.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፤ በአላህ አጋሪዎች እርኩሶች ብቻ ናቸው። እናም ከዚህ ዓመታቸው* በኋላ ወደ ተከበረው መስጊድ እንዳይቀርቡ። ድህነትን ብትፈሩ አላህ ቢፈልግ ከችሮታው ያከብራችኋል። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «እናንተ አይሁድ እስከምትታገሉ ድረስና አይሁድ ከጀርባው የሚደብቁበትን ቋጥኝ፤ ድንጋይና ዛፍ እንኳን ሳይቀር «ሙስሊሞች ሆይ! እዚህ ከኔ ኋላ አይሁዳዊ ሰው ተደብቋልና ግደለው» ብሎ እስኪናገር ድረስ የትንሳኤ ቀን አይከሰትም።»

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ (28) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙሽሪኮች ወደ መካ ምግብ ይዘው እየመጡ ይነግዱ ነበር። ወደ ካዕባ እንዳይመጡ በተከለከሉ ጊዜ ሙስሊሞች «ከየት ልንመገብ» ነው በማለት ስለ ጠየቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

**ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (13-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙስሊሞች መስፈርቱ በተሟላ ላይ እንዲሳተፉ ጥሪና ቅስቀሳ ማድረግ ኢስላማዊ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
2. የአላህን ፍራቻ በልብ ውስጥ ማሳደር ኢስላማዊ ግዴታ ስለመሆኑ፤
3. የእምነት ከልብ ሰርፆ መግባባትና ለኢስላማዊ ተግባራት ትግል ደፋር ሆኖና ጀግና ሆኖ መገኘት ተያያዥነት ያላቸው መሆናቸውን፤
4. መስፈርቱ የተሟላው ጂሃድ ሕዝቦች በብዛትና በቡድን ወደ ኢስላም እንዲገቡ በር የሚከፍት ስለ መሆኑ፤
5. አስገዳጅ ነገሮች ተፈጥረው ሙስሊሞች ካልፈቀዱ በስተቀር አንድ ከሃዲ ወደ አላህ ቤት መስጊድ ውስጥ ዘልቆ መግባቱ የተከለከለ ስለመሆኑ፤
6. መስጊድን መገንባትና የመስጊድን ንፅህና መጠበቅ ከፍተኛ ምንዳ ያለው ኢስማዊ ተግባር ስለመሆኑ፤
7. በአላህ እና በመጨረሻው ቀን ማመን፤ ሶላትን ዘወትር መስገድ፤ ዘካን ለተገቢው ሰው በተገቢው ሁኔታ መስጠት መሠረታዊ የሆኑ የሃይማኖቱ የእምነት ክፍሎችና ግዴታዎች ስለ መሆናቸው፤
8. ከምዕመናን ሁሉ የተሟላ እምነት አላቸው ተብለው የሚፈረጁት የአላህ ቅርብ ወዳጆችና ቅን አገልጋዮች ማለት የትኞች ሰዎች እንደሆኑ፤
9. መስፈርቱ ለተሟላው ጂሃድ እና ለሃይማኖት ብሎ መሰደድ ያለውን መጠነ ሰፊ ምንዳ፤
10. ወንጀልን የሚያዘወትሩ ሰዎች በኃጢአት የተዘፈቁ ቀንደኞች የአላህን መመራት ለማግኘት ያላቸው ዕድል የጠበበ መሆኑን፤
11. ከከሓዲያን ጋር ልባዊ ወዳጅነትን መመስረት እጅግ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
12. አላህንና መልዕክተኛውን (ﷺ) እንዲሁም ትክክለኛ አማኞችን በጠላትነት መመልከትና በጠላትነት መፈረጅ የግፎች ሁሉ ግፍ ታላቅ ወንጀል ስለመሆኑ፤
13. በምላስም ሆነ በተግባር የክህደት ተግባራትን መፈፀም የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
14. አላህ ምእመናን የሰጠውን ክብርና ማዕረግ፤
15. ለጂሀድ መቀስቀስ ምክንያት የሚሆኑት ጉዳዮች ምን ምን እንደሆኑ፤
16. የከሓዲያን የመንፈስ ዝቅጠት ምን ያህል የከፋ ስለ መሆኑ፤
17. በአላህና በረሱል ሙሐመድ (ﷺ) ያላመኑ ከሓዲያን ከዘጠነኛው ዓመተ ሒጅራ በኋላ ወደ መካ ከተማ እንዳይገቡ መደረጋቸውን፤
18. ማንኛውም ሙእሚን በቁሳዊ ሀብቶች ድሃ መሆኑ ከዒባዳ ተግባራት የማይከለከለው መሆኑን እንማራለን።

قَٰتِلُواْ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَلَا بِٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِ وَلَا يُحَرِّمُونَ مَا حَرَّمَ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ
وَلَا يَدِينُونَ دِينَ ٱلۡحَقِّ مِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ حَتَّىٰ يُعۡطُواْ ٱلۡجِزۡيَةَ عَن يَدٖ
وَهُمۡ صَٰغِرُونَ ٢٩ وَقَالَتِ ٱلۡيَهُودُ عُزَيۡرٌ ٱبۡنُ ٱللَّهِ وَقَالَتِ ٱلنَّصَٰرَى ٱلۡمَسِيحُ ٱبۡنُ ٱللَّهِۖ ذَٰلِكَ
قَوۡلُهُم بِأَفۡوَٰهِهِمۡۖ يُضَٰهِـُٔونَ قَوۡلَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن قَبۡلُۚ قَٰتَلَهُمُ ٱللَّهُۖ أَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ٣٠
ٱتَّخَذُوٓاْ أَحۡبَارَهُمۡ وَرُهۡبَٰنَهُمۡ أَرۡبَابٗا مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَٱلۡمَسِيحَ ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا
لِيَعۡبُدُوٓاْ إِلَٰهٗا وَٰحِدٗاۖ لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ سُبۡحَٰنَهُۥ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٣١

**29-31.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ከእነዚያ መጽሐፍን ከተሰጡ ሰዎች መካከል እነዚያን በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑትን ክፍሎች አላህና መልዕክተኛው እርም ያደረጉትንም እርም የማያደርጉትን፤ እውነተኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉትን እነርሱ የተዋረዱ ሆነው ግብርን በእጆቻቸው እስከሚሰጡ ድረስ ተዋጓቸው።* አይሁዶች ኡዘይር የአላህ ልጅ ነው አሉ። ክርስቲያኖችም አል-መሲህ የአላህ ልጅ ነው አሉ። ይህ በአፎቻቸው የሚናገሩት ፀያፍ ቃላቸው ነው። የእነዚያን ከእነርሱ በፊት በአላህ የካዱት ሰዎች ቃል ያመሳስላሉ። አላህ ያጥፋቸው። ከእውነት እንዴት ያፈነግጣሉ!። (አይሁድና ክርስቲያኖች) ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለውን አንዱን አምላክ አላህን ብቻ ሊገዙ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆኑ ሊቃውንቶቻቸውን፣ መነኮሳቶቻቸውንና የመርየምን ልጅ አልመሲሕንም ከአላህ ሌላ አማልክት አድርገው ያዙ። ከእርሱ በስተቀር ትክክለኛ አምላክ የለም። አላህ ግን ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።

* (31) ኛው አንቀፅ በወረደ ጊዜ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ "ነብዩ (ﷺ) ዐዲይ ኢብኑ ሃቲም ለተባለው ሱሃቢይ ሲያነቡለት ሁኔታው ገርሞት «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እኛ እኮ እነርሱን አናመልካቸውም» በማለት ሲናገር "አላህ ሀራም ያለውን ሀላል፤ ሀላል ያለውን ደግሞ ሀራም ሲሉ ትቀበሏቸው አልነበረምን?" ሲሉ ጠየቁት። እርሱም «እሱንማ አዎ»አላቸው። ነብዩም (ﷺ) «ታዲያ እነርሱን ማምለክ ማለት ይኸው አይደለም እንዴ» ሲሉ መለሱለት። የሚል ተዘግቧል።

የአንድ ሙጅተሂድ ዐሊም ንግግር ከቁርኣንና ሐዲስ ጋር የሚጣጣም ከሆነ መቀበል፤ ተቃርኖ የተገኘ ከሆነ ደግሞ መተው ተገቢ ነው። ታላላቅ የኢስላም ዑለሞች ይህንኑ ተናግረዋል፦ ኢማም አቡ ሃኒፋ እንዲህ ማለታቸው ተመልክቷል «ከአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) መምጣቱ ከተረጋገጠ ያለምንም ማመንታት እንቀበለዋለን። ከሶሀባ መገኘቱ ከታወቀም እንቀበለዋለን። ከታቢዒይ የተገኘ ከሆነ ግን እኛም ሰዎች ነን (እናነባለን መረጃዎችን እንፈትሻለን) እነርሱም ሰዎች ናቸው።»

አቡ ሃኒፋ እኛም በማለት የገለፁት ቃል የሚወክለው እርሳቸውንና መሰል የዒልም እኩዮቻቸውን ነው። አንዳንድ ገና ምኑንም የማያውቁ ተማሪዎች የኚህን ታላቅ ኢማም ንግግር ያለ አግባብ ሲጠቀሙበት ይስተዋላል። ራሳቸውን ከታላላቅ ምሁራን ተርታ ማሰለፍ ይቃጣቸዋል።

የአቡ ሃኒፋ ዓላማ መሐይማንን ከዑለሞች ተርታ ማሰለፍ እንዳልሆነ ግልፅ ነው።

ኢማሙ ማሊክ እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ "ሁላችንም ንግግሩ ተቀባይነት ሊያገኝ ወይም ውድቅ ሊደረግ ይችላል።»

ኢማሙ ሻፊዒይ እንዲህ ብለዋል፦

1. "ሐዲሱ ሶሒሕ ሆኖ ከተገኘ የእኔ መዝሐብ ነው። "
2. "ንግግሬ ከመልዕክተኛው ሙሐመድ (ﷺ) ንግግር ጋር ተቃርኖ ከተገኘ ከአጥር በስተጀርባ ወርውሩት። "

ኢማሙ አህመድ ቢን ሐንበል እንዲህ ብለዋል። "የአንድን ሐዲስ ሰነድ ተአማኒነት ያወቁ የሱፍያንን ንግግር ቅድሚያ የሚሰጡ ሰዎች እጅግ ያስደንቁኛል። አላህ፦ "እነዚያ የእርሱን ትዕዛዝ የሚቃረኑ ሰዎች...»ብሏል። (አን-ኑር:73) አብደላህ ኢኢብኑ ዐባስ እንዲህ ብለዋል፦ "ምን አልባትም ከሰማይ ድንጋይ ይዘንብባችሁ ይሆናል። የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (ﷺ) እንዲህ አሉ። «ስለ እናንተ

አቡበክር ወይም ዑመር እንዲህ ብሏል ትሉኛላችሁ» አብዱራህማን ኢብኑ ሐሰን “ፈትሁል መጂድ” በተሰኘው ኪታባቸው እንዲህ ሲሉ ፅፈዋል:- «እያንዳንዱ ለአቅመ አዳም የደረሰ ሙስሊም ትክክለኛ የሐዲስ ዘገባ ከደረሰውና ትርጉሙን ከተረዳ ሊቀበለውም ሊሰራበትም ይገባል። ማንም ቢቃረነውም ብልህ ሰው የዑለሞችን ንግግር ካነበበ፤ ከፈተሸና ከተረዳ በቁርአንና ሐዲስ ለመመዘን ይሞክራል። እያንዳንዱ ዑለማ ሙጅተሂድ እና ተማሪዎቻቸው ለንግግራቸው ከቁርአንና ከሐዲስ ዋቢዎችን ይዘክራሉ። በአንድ ጉዳይ ላይ እውነታው አንድ ነው። ዑለሞች ኢጅቲሐድ በማድረጋቸው ከአላህ ዘንድ ምንዳ ያገኛሉ። በሳል ጭንቅላት ያለው ሰው የሰጡትን አስተያየት ይፈትሻል፤ ይመረምራል። እውነታው ላይ ለመድረስ የሚቀርበውን መረጃ ተንተርሶ፤ በመጨረሻም ይበልጥ ጠንካራ መረጃ ያቀረበውን ዑለማ አስተያየት ይቀበላል። “ከታዘዛችኋቸው ሙሽሪኮች ናችሁ” (የእንስሳት ምዕራፍ፡ **121**) የሚለውን የቁርኣን አንቀፅ በማስመልከትም እንዲህ ብለዋል:- “ብዙ ሰዎች እዚህ ጥፋት ላይ ይወድቃሉ። የአንዳንድ ሰዎች ንግግር ይቀበላሉ። ይከተላሉ። ያን ንግግር ተቃርነው ለሚመጡ መረጃዎች ክብደት አይሰጡም። ይህ ታላቅ የሽርክ ተግባር ነው። በዚህ ባህሪ ከፅንፈኝነት ደረጃ ደረሱ። ይበልጥ ጠንካራ መረጃ ያለውን ሀሳብ መከተል ይጠላል ወይም ሐራም ነው ብለው ያስባሉ። ይህ ትልቅ ፈተና ነው። (ተቃራኒ ሐሳብ ያለበትን ወገኖች):- “እነርሱ ከኛ ይበልጥ ጠንካራ መረጃ ይዘዋል...” ይላሉ።

“ነገሮች ይህን ያህል አስከፊ በሆነ ሁኔታ ተለዋውጠዋል። አዋቂ የህብረተሰብ ክፍሎችን ማምለክ ከታላላቅ የፅድቅ ተግባራት እንደሚፈረጅ በርካታ ሰዎች ያስባሉ። ይህን እምነታቸውን “ዊላያ” የሚል ስያሜ ይሰጡታል። ዑለሞችን ማምለክ እውቀት ሆኗል። ቀስ በቀስ ጻድቅ ያልሆነ ሰዎችን ከአላህ ውጭ ማምለክ ጀመሩ። አላዋቂ ሰዎችም ተመለኩ...” አሳሳች ዑለሞች በዚህ ዲን ላይ የጨመሩትን የቢድዓ ድሪቶ መቀበልህና እነርሱን መታዘዝም ከዚሁ ውስጥ የሚፈረጅ ነው። እነኚህ አሳሳች ዑለሞች አላህ ያልፈቀደውን ነገር ደነገጉ። መሐይማን ተከተሏቸው። ሱና ነው በሚል እምነት። ያንን የሚከተሉትን ነገሮች ያወገዘንና ነብዩ ያስተማሩትን ጉዳይ ይከተሉ ዘንድ ጥሪ ያደረገን ሰው ከዲን የወጣ ያህል ይመለከቱታል። ዑለማዎችንና ደጋግ ሰዎችን እንደሚጠላ ይቆጥሩታል። መልካሙ ነገር እንደከፋ፤ ከፉው ነገር እንደ መልካም ይታያል። ሱንናው ቢድዓ ቢድዓው ደግሞ ሱና ሆነ። ሰዎች ይህንን የተበረዘ እምነት እንደያዙ እድሜያቸውን ይጨርሳሉ። ይህ የሚያመለክተው ኢስላም ምን ያህል እንደተረሳና ትክክለኛ ዳዒዎች አናሳ መሆናቸውን ነው። ታላላቅ የፊቅህ ምሁራን የበኩላቸውን ምርምርና ፍተሻ አድርገው በሰጡት ብይን ስህተት ከፈፀሙ ምንዳ የሚያገኙ ቢሆንም ስህተት በፈፀሙበት ነጥብ ላይ እነሱን መከተል አይፈቀድም ይህ ከሆነ ደግሞ አሳሳች ዑለሞችን እጅቲሃድ ማድረግ ሲገባ በዐቂዳ መከተል ሀራምነቱ ይበልጥ የገዘፈ ነው። ዓቂዳን በተመለከተ ማንም ምንም የማለት ሙብት የለውም። የዓቂዳ ምንጭ ግልፅና የማያሻማ የቁርኣን አንቀፅ ብቻ ነው። ግና ሁኔታዎች አስከፊ ሆነዋል።

ይህ አንቀፅ ኢስላምን የጠላው ቢጠላው ማሸነፉና ይፋ መውጣቱ የማይቀር ሀቅ መሆኑን ከሚያበስሩ አያሌ አናቅፆች መካከል አንዱ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ ትምህርት ከሰጡ አናቅፅ መካከል:- በፈትህ ም. **(28)** ኛው አንቀፅ፤ በፋጢር ም. **10** ኛው አንቀፅ፤ በአል. ሙጃደለህ ም. **(20)**. **(21)** ኛው አንቀፅና በአስሷፋት ም. **(171)**. **(182)** አንቀፅ ያሉት አናቅፅ ከሚጠቀሱት ጥቂቶች ናቸው።

እነዚህን አናቅፅ በጥሞና ያጤናቸው ሰው የሚገነዘበው ነገር ቢኖር እውነት የቱንም ያህል ቢዳከም የኋላኋላ ድል ማድረጉ የማይቀር ከአላህ ዋስትና የተሰጠው መሆኑን ነው። ነብዩ (ﷺ) «ይህ ጉዳይ ፀሐይና ጨረቃ የደረሱበት ድረስ ሁሉ ይደርሳል። የአፈር ቤትም ሆነ የድንጋይ ቤት የተዋረደው ተዋርዶ የተከበረው ተከብሮ ይህ ዲን መግባቱ አይቀሬ ነው» ብለዋል።

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ **(30)** ዐኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-

የአይሁድ አመራሮች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው (አንተ ቂብላችንን ትተህ ኡዘይር የአላህ ልጅ ነው ሳትል እንዴት እንከተልሀለን) በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

يُرِيدُونَ أَن يُطۡفِـُٔواْ نُورَ ٱللَّهِ بِأَفۡوَٰهِهِمۡ وَيَأۡبَى ٱللَّهُ إِلَّآ أَن يُتِمَّ نُورَهُۥ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴿٣٢﴾
هُوَ ٱلَّذِيٓ أَرۡسَلَ رَسُولَهُۥ بِٱلۡهُدَىٰ وَدِينِ ٱلۡحَقِّ لِيُظۡهِرَهُۥ عَلَى ٱلدِّينِ كُلِّهِۦ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡمُشۡرِكُونَ ﴿٣٣﴾

**32-33.** (ከሓዲያን) የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ለማጥፋት ይፈልጋሉ። አላህ ከሓዲያን ቢጠሉም እንኳ ብርሃኑን መሙላትን እንጂ ሌላን አይሻም። (እርሱ) ያ!አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልዕክተኛውን (ሙሐመድን) በቅን መንገድና በእውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደርገው ዘንድ የላከ ብቸኛ አምላክ ነው።

۞يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلۡأَحۡبَارِ وَٱلرُّهۡبَانِ لَيَأۡكُلُونَ أَمۡوَٰلَ ٱلنَّاسِ بِٱلۡبَٰطِلِ
وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِۗ وَٱلَّذِينَ يَكۡنِزُونَ ٱلذَّهَبَ وَٱلۡفِضَّةَ وَلَا يُنفِقُونَهَا فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ
فَبَشِّرۡهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٖ ﴿٣٤﴾ يَوۡمَ يُحۡمَىٰ عَلَيۡهَا فِي نَارِ جَهَنَّمَ فَتُكۡوَىٰ بِهَا جِبَاهُهُمۡ وَجُنُوبُهُمۡ
وَظُهُورُهُمۡۖ هَٰذَا مَا كَنَزۡتُمۡ لِأَنفُسِكُمۡ فَذُوقُواْ مَا كُنتُمۡ تَكۡنِزُونَ ﴿٣٥﴾

**34-35.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ከሊቃውንትና ከመነኮሳት ብዙዎቹ የሰዎችን ገንዘቦች በውሸት ይበላሉ። ከአላህ መንገድም ሰዎችን ያግዳሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ወርቅንና ብርን የሚያደልቡትን በአላህ መንገድ ላይ በማያወጧቸው ሰዎች በአሳማሚ ቅጣት አብስራቸው። (በብሩና በወርቁ ላይ) በገሀነም እሳት ውስጥ በሚግሉበትና ግንባሮቻቸው ጀርቦቻቸው በእርሱ በሚተኮሱበት ቀን (አሳማሚ በሆነ ቅጣት) አብስራቸው። ይህ ለነፍሶቻችሁ ያደለባችሁት ነው። ታደልቡት የነበራችሁትንም ቅመሱ (ይባላሉ)።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (34) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:-
ከህዝቦቻቸው የፍታት እያሉ ጉቦ መሰል ገንዘብ ጥቅማጥቅም ሲበሉ በነበሩ የመዲና መፅሐፍ ቁዱስ አዋቂ ነን ባዮች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

إِنَّ عِدَّةَ ٱلشُّهُورِ عِندَ ٱللَّهِ ٱثۡنَا عَشَرَ شَهۡرٗا فِي كِتَٰبِ ٱللَّهِ يَوۡمَ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ
مِنۡهَآ أَرۡبَعَةٌ حُرُمٞۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلۡقَيِّمُۚ فَلَا تَظۡلِمُواْ فِيهِنَّ أَنفُسَكُمۡۚ وَقَٰتِلُواْ ٱلۡمُشۡرِكِينَ كَآفَّةٗ
كَمَا يُقَٰتِلُونَكُمۡ كَآفَّةٗۚ وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلۡمُتَّقِينَ ﴿٣٦﴾ إِنَّمَا ٱلنَّسِيٓءُ زِيَادَةٞ فِي ٱلۡكُفۡرِۖ
يُضَلُّ بِهِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُحِلُّونَهُۥ عَامٗا وَيُحَرِّمُونَهُۥ عَامٗا لِّيُوَاطِـُٔواْ عِدَّةَ مَا حَرَّمَ ٱللَّهُ
فَيُحِلُّواْ مَا حَرَّمَ ٱللَّهُۚ زُيِّنَ لَهُمۡ سُوٓءُ أَعۡمَٰلِهِمۡۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿٣٧﴾

**36-37.** የወራት ቁጥር አላህ ዘንድ በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ሰማያትንና ምድርን በፈጠረበት ቀን አስራ ሁለት ወር ብቻ ነው። ከእነርሱም መካከል አራቱ* የተከበሩ ወሮች ናቸው። ይህ ቀጥተኛው ሃይማኖት ነው። በእነርሱ ውስጥም ክብሮቻቸውን በመጣስ ነፍሶቻችሁን አትበድሉ። አጋሪዎችንም በአንድ ላይ ሆነው እንደሚጋደሏችሁ በአንድ ላይ ሆናችሁ ተጋደሏቸው። አላህ በእርዳታው ከሚፈሩት ጋር መሆኑን እወቁ። የአንዱን ወር ክብር ወደ ሌላው ማዘግየት በክህደት ላይ ክህደትን መጨመር ነው። በዚህ ተግባር ላይ እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ይሳሳቱበታል። በአንደኛው ዓመት የተፈቀደ ያደርጉታል። በሌላው ዓመት ደግሞ ያወግዙታል። ይህ አላህ ያከበራቸውን ወሮች ቁጥር ሊያስተካከሉና አላህ እርም ያደረገውን የተፈቀደ ሊያደርጉ ነው። መጥፎ ሥራዎቻቸው ለእነርሱ ተዋበላቸው። አላህ ከሓዲያን ህዝቦችን ወደ ቀናው መንገድ አይመራም።

* የዐረብኛ ወራቶች ሙሀረም፣ ሶፈር፣ ረቢየል አውል፣ ረበዐል ሳኒ፣ ጁማደል አወል፣ ጀማደል ሳኒ፣ ረጀብ፣ ሻባን፣ ረመዳን፣ ሸዋል፣ ዙልቀዕዳ፣ ዙልሂጃ ናቸው። አራት የተባሉት ዙልቀዕዳ፣ ዙልሂጃ፣ ሙሀረምና ረጀብ ናቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَا لَكُمۡ إِذَا قِيلَ لَكُمُ ٱنفِرُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ ٱثَّاقَلۡتُمۡ إِلَى ٱلۡأَرۡضِۚ أَرَضِيتُم
بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا مِنَ ٱلۡأٓخِرَةِۚ فَمَا مَتَٰعُ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا فِي ٱلۡأٓخِرَةِ إِلَّا قَلِيلٌ ٣٨ إِلَّا تَنفِرُواْ
يُعَذِّبۡكُمۡ عَذَابًا أَلِيمٗا وَيَسۡتَبۡدِلۡ قَوۡمًا غَيۡرَكُمۡ وَلَا تَضُرُّوهُ شَيۡـٔٗاۗ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ٣٩

**38-39.** እናንተ በትክክል በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ በአላህ መንገድ ለመታገል ዝመቱ በተባላችሁ ጊዜ ወደ ምድር የምትወዘፉት ለምንድን ነው? የቅርቢቱን ህይወት ከመጨረሻይቱ ህይወት ይበልጥ ወደዳችሁን? የቅርቢቱ ህይወት ጥቅም ከመጨረሻይቱ ህይወት አንፃር ጥቂት እንጂ ምንም* አይደለም። (አማኞች ሆይ)፣ ለዘመቻ ባትወጡ አላህ አሳማሚ ቅጣት ይቀጣችኋል። ከናንተ ሌላ የሆኑን ህዝቦችም ይለውጣል። አላህን በምንም አትጎዱትም። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም ሰው ከሞተ በኋላ መልካም ነገሮች ከአላህ ዘንድ አግኝቶ ወደ ምድር ላይ ነገሮችን ማግኘቱ የማያስደስተው የለም። በአላህ መንገድ ላይ መስዋእት ከሆነ ሰው በስተቀር። ይህ ሰው ወደ ምድር ተመልሶ በአላህ መንገድ ላይ ዳግመኛ መሞቱ ያስደስተዋል።»

ከንሰሓ መግባት ከ (38-39) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሙስሊሞች ወደ ተቡክ ዘመቻ እንዲሄዱ ሲታዘዙ ግዜው ሞቃትና አዝመራው ያፈራበት ወቅት ስለነበር ብዙዎች በዚህ ወቅት ዘመቻ መውጣቱ ከበዳቸው። በዚህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ፣ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِلَّا تَنصُرُوهُ فَقَدْ نَصَرَهُ ٱللَّهُ إِذْ أَخْرَجَهُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ثَانِىَ ٱثْنَيْنِ إِذْ هُمَا فِى ٱلْغَارِ إِذْ يَقُولُ لِصَٰحِبِهِۦ لَا تَحْزَنْ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَنَا ۖ فَأَنزَلَ ٱللَّهُ سَكِينَتَهُۥ عَلَيْهِ وَأَيَّدَهُۥ بِجُنُودٍ لَّمْ تَرَوْهَا وَجَعَلَ كَلِمَةَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ٱلسُّفْلَىٰ ۗ وَكَلِمَةُ ٱللَّهِ هِىَ ٱلْعُلْيَا ۗ وَٱللَّهُ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٤٠﴾

**40.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ነብዩን (ሙሐመድን) ባትረዱት እነዚያ በአላህ የካዱት ህዝቦች የሁለት ሰዎች ሁለተኛ ሆኖ ከመካ ባስወጡት ጊዜ አላህ ረድቶታል። ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህ እርካታውን በእርሱ ላይ አወረደ። ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው። የእነዚያን በአላህ የካዱትን ሰዎች ቃል የበታች አደረገ። የአላህ ቃል ግን የበላይ ነው። አላህ ሁሉን አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

**ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ ከ (34-40) ካሉ አናቅፅ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋናዋናዎቹ፡**

1. የአይሁድ ምሁራን የተበላሸን ውስጣዊ ማንነት የሚያጋልጥ ቁርአናዊ አንቀፅ፤
2. የሰውን ገንዘብና ንብረት ያለ አግባብ መብላት ክልክል ስለመሆኑ፤
3. ዘካ ሳይከፍሉ ሀብትን ማካበት የተከለከለ ስለመሆኑ፤
4. ዘካ የተከፈለበት ሀብት የሚበረክትና ምንም ችግር የማያስከትል መሆኑ፤
5. በዓመቱ ውስጥ የሚገኙት የወራት ብዛት (12) ብቻ እንደሆኑና ከእነዚህ 12 ከአመቱ ወራት ውስጥ አራቱ የተከበሩ ተብለው እንደሚጠሩና በእነኚህ የተከበሩ ወራት ውስጥ ከጠላት በኩል ካል ተገፉ በስተቀር ጦርነት ማካሄድ የተከለከለ መሆኑ፤
6. አላህ ምንግዜም ፍጡራኖቹን ባጠቃላይ የሚጠብቅና ፍጡራኖቹ በሙሉ በእርሱ ቁጥጥርና ጥበቃ ስር እንደሆኑ፤
7. በሀይማኖት ላይ ዘዴን ተጠቅሞ መገለባበጥ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
8. በክህደት ዘውታሪሆኖ ህይወትን በተሳሳተ ጎዳና ለረጅም ጊዜ መምራት ለሂዳያ (ለመምራት) እድልን የሚያጠብ ስለ መሆኑ፤
9. የሙስሊሙ ህዝብ መሪ የጂሀድ ጥሪ ካስተላለፈ ወደ ጂሃድ መውጣት በሙስሊሞች አንድነት ላይ የተጣለ ግዴታ መሆኑን፤
10. ዱንያ ከአኼራ ጋር ስትነፃፀር እዚህ ግባ የሚባል ግምት የማይሰጣት ትንሽ ጠፊና ጊዜያዊ ዓለም መሆኗን፤
11. በነብዩ (ﷺ) ጊዜ የነበሩ ጓዶቻቸው በማንኛውም ጉዳይ ላይ ረሱል (ﷺ) ተግባራዊ ያደረጉትን ተግባራዊ ያደርጉ እንደነበር፤
12. አቡበክር ከአላህ ትላቅ ክብርና ማዕረግ የተሰጣቸውና ሃይማኖቱንም በጣም የረዱ ሱሀባ መሆናቸውን፤
13. ሐዘን የአላህን ምርጥ ባሮችንም እንደ አቡበክር ያሉትን እንኳን ሳይቀር ሊያጋጥማቸው እንደሚችል፤
14. ወራትን መቀያየር ክህደት ስለ መሆኑና ብሎም ሐራምን ሐላል ማድረግ ሽርክ ስለመሆኑ፤
15. መረጋጋት በተለይም በሐዘን ጊዜ አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
16. ኢስላም ከየትኛቹም ሃይማኖቶች በሙሉ የበላይ ሃይማኖት መሆኑን እንማራለን።

ٱنفِرُواْ خِفَافًا وَثِقَالًا وَجَٰهِدُواْ بِأَمْوَٰلِكُمْ وَأَنفُسِكُمْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِۚ
ذَٰلِكُمْ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٤١﴾

**41.** (አማኞች ሆይ)፣ ቢቀላችሁም ቢከብዳችሁም ዝመቱ። በአላህ መንገድ በገንዘቦቻችሁና በነፍሶቻችሁ ታገሉ ይህ ተግባር የምታውቁ ከሆናችሁ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው።

لَوْ كَانَ عَرَضًا قَرِيبًا وَسَفَرًا قَاصِدًا لَّٱتَّبَعُوكَ وَلَٰكِنۢ بَعُدَتْ عَلَيْهِمُ ٱلشُّقَّةُۚ وَسَيَحْلِفُونَ
بِٱللَّهِ لَوِ ٱسْتَطَعْنَا لَخَرَجْنَا مَعَكُمْ يُهْلِكُونَ أَنفُسَهُمْ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ إِنَّهُمْ لَكَٰذِبُونَ ﴿٤٢﴾ عَفَا
ٱللَّهُ عَنكَ لِمَ أَذِنتَ لَهُمْ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَكَ ٱلَّذِينَ صَدَقُواْ وَتَعْلَمَ ٱلْكَٰذِبِينَ ﴿٤٣﴾ لَا يَسْتَـْٔذِنُكَ
ٱلَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْأَخِرِ أَن يُجَٰهِدُواْ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْۗ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِٱلْمُتَّقِينَ ﴿٤٤﴾

**42-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የጠራህባቸው ነገር ቅርብ ጥቅምና መካከለኛ ጉዞ በሆነ ኖሮ በተከተሉህ ነበር። ግን በእነርሱ ላይ መንገዲቱ ራቀችባቸው። በቻልንም ኖሮ ከናንተ ጋር በወጣን ነበር ሲሉ በአላህ ይምላሉ። እራሳቸውን ለጥፋት (በውሸት) ይዳርጋሉ አላህ እነርሱ ውሸታሞች መሆናቸውን ጠንቅቆ ያውቃል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ካንተ ይቅር ብሎሀል። እነዚያ እውነተኞቹ እስከሚገለፁልህና ውሸታሞቹን ለይተህ እስከምታውቅ ድረስ ለእነርሱ ከዘመቻ እንዲቀሩ ለምን ፈቀድክላቸው? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው ከመታገላቸው ለመቅረት ፈቃድን አይጠይቁህም። አላህ በትክክል የሚፈሩትን ሰዎች ሁሉ አዋቂ ነው።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከ (42-43) ኛ ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:-

ነብዩ (ﷺ) ወደ ተቡክ ዘመቻ ለመውጣት ሲያስቡ ድንኳናቸውን ሰኒየተል ወዳዕ የሚባለው ጋራ ላይ ተከሉ። አብደላህ ኢብኑ ኡበይም ከዚያው ዝቅ ብሎ ዚሂዳ የምትባል ቦታ ላይ ድንኳኑን ተከለ። ነብዩ (ﷺ) ዝግጅታቸውን ጨርሰው ጉዞአቸውን ሲጀምሩ አብደላህ ብኑ ኡበይ በበኩሉ አስመሳዮችን አሠባስቦ ቀረ። በዚህ ጉዳይ ነብዩ (ﷺ) እንዳያዝኑ ለማፅናናት ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

إِنَّمَا يَسْتَـْٔذِنُكَ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْأَخِرِ وَٱرْتَابَتْ قُلُوبُهُمْ فَهُمْ فِي رَيْبِهِمْ
يَتَرَدَّدُونَ ﴿٤٥﴾ ۞ وَلَوْ أَرَادُواْ ٱلْخُرُوجَ لَأَعَدُّواْ لَهُۥ عُدَّةً وَلَٰكِن كَرِهَ ٱللَّهُ ٱنۢبِعَاثَهُمْ فَثَبَّطَهُمْ
وَقِيلَ ٱقْعُدُواْ مَعَ ٱلْقَٰعِدِينَ ﴿٤٦﴾ لَوْ خَرَجُواْ فِيكُم مَّا زَادُوكُمْ إِلَّا خَبَالًا وَلَأَوْضَعُواْ
خِلَٰلَكُمْ يَبْغُونَكُمُ ٱلْفِتْنَةَ وَفِيكُمْ سَمَّٰعُونَ لَهُمْۗ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٤٧﴾

**45-47.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ፈቃድ የሚጠይቁህ እነዚያ በአላህና በመጨረሻው ቀን የማያምኑት፣ ልቦቻቸው የተጠራጠሩት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነርሱም በጥርጣሬያቸው ውስጥ ይዋልላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ ዘመቻ መውጣት ባሰቡ ኖሮ ለእርሱ ዝግጅትን ባሰናዱ ነበር። ግን አላህ ለመውጣት እንቅስቃሴያቸውን ጠላውና አሰነፋቸው። ከተቀማጮቹ ጋር ተቀመጡ ተባሉም። (አማኞች ሆይ)፣ ከናንተ ጋር በወጡ ኖሮ ጥፋትን እንጂ አይጨምሩላችሁም ነበር። ሁከትንም የሚፈልጉላችሁ ሲሆኑ በመካከላችሁ ነገር በማሳበቅ ይቻኮሉ ነበር። በእናንተ ውስጥ ለእነርሱ አዳማጮች አሏቸው። አላህ በዳዮችን አዋቂ ነውና።

لَقَدِ ٱبْتَغَوُا۟ ٱلْفِتْنَةَ مِن قَبْلُ وَقَلَّبُوا۟ لَكَ ٱلْأُمُورَ حَتَّىٰ جَآءَ ٱلْحَقُّ وَظَهَرَ أَمْرُ ٱللَّهِ وَهُمْ
كَٰرِهُونَ ﴿٤٨﴾ وَمِنْهُم مَّن يَقُولُ ٱئْذَن لِّى وَلَا تَفْتِنِّىٓ ۚ أَلَا فِى ٱلْفِتْنَةِ سَقَطُوا۟ ۗ وَإِنَّ جَهَنَّمَ
لَمُحِيطَةٌۢ بِٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٤٩﴾ إِن تُصِبْكَ حَسَنَةٌ تَسُؤْهُمْ ۖ وَإِن تُصِبْكَ مُصِيبَةٌ يَقُولُوا۟ قَدْ أَخَذْنَآ
أَمْرَنَا مِن قَبْلُ وَيَتَوَلَّوا۟ وَّهُمْ فَرِحُونَ ﴿٥٠﴾

**48-50.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱ ጠይዎች ሲሆኑ እውነቱ እስከመጣና የአላህ ትዕዛዝ እስከተገለፀ ድረስ ከዚህ በፊት ሁከትን በእርግጥ ፈለጉ። ነገሮችን ሁሉ አገላበጡልህ። ከእነርሱም ውስጥ ለእኔ ፍቀድልኝ አትሞክረኝ የሚል ሰው አለ። (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተውሉ። እኒህ ሰዎች በመከራ ውስጥ ወደቁ። ገሀነም ከሓዲዎችን ከባቢ ናት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መልካም ነገር ቢያገኝህ ያስከፋቸዋል። መከራ ቢያገኝህ ግን ፊቱንም ይህን ፈርተን የግል ጥንቃቄያችንን ይዘናል ይላሉ። ተደሳቾች ሆነውም ይሸሻሉ።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (50) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ከተቡክ ዘመቻ የቀሩ አስመሳዮች በነብዩ (ﷺ) እና በተከታዮቻቸው ላይ መጥፎ ነገር እንደደረሰባቸው አስወሩ። በኋላ ነገሩ በተቃራኒው መሆኑ ሲረጋገጥ በጣም ስለተከፋ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፣ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (41-48) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የሙስሊሞች መሪ የጂሃድ ጥሪ አዋጅ ካስተላለፈ መሸሸና ማፈግፈግ ወንጀል መሆኑን፣
2. በሕይወት ብቻ ሳይሆን ለጂሃድ ማስፈፀሚያ የሚውል ገንዘብ በመለገስም የጂሃድ ተሳታፊ መሆን እንደሚቻል፣
3. በኢስላም በሀሰት መማል ለአሰቃቂ ቅጣት እንደሚዳርግ፣
4. የወደዱት ሰው በስህተት ላይ ሲገኝ መገሰፅና ከስህተቱ እንዲታረም መውቀስ ተገቢ ስለሆነ፣
5. ነብዩ (ﷺ) የሰው ልጅ እንደመሆናቸው እያንዳንዱን ነገር ለማወቅ እንደማይችሉ፣

6. እምነት ና የአላህ ፍራቻ ለሰው ልጅ የሚያጎናፅፉትን ክብርና ማዕረግ፤
7. በሙሉ ልብ አላህን ማመንና ኢስላምን መቀበል ግዴታ መሆኑን፤
8. የአስመሳዮች ተንኮል ሙስሊሞችን ለመጥፎ አደጋና ለከፋ ጉዳት የሚዳርግ ስለመሆኑ፤
9. ወሳኝ በሆኑ ሃይማኖታዊና ሌሎች ጉዳዮች ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ጉዳዩን ውጤታማ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ ግዴታ ስለመሆኑ፤
10. አስመሳዮች የሙስሊሞች መጠናከርና ኃያል መሆን የሚያስከፋቸው መሆኑን፤
11. የአላህን ውሳኔና ቅንብር ያለምንም ቅሬታ መቀበል ግዴታ መሆኑን እንማራለን።

قُل لَّن يُصِيبَنَآ إِلَّا مَا كَتَبَ ٱللَّهُ لَنَا هُوَ مَوۡلَىٰنَاۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلۡيَتَوَكَّلِ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ﴿٥١﴾ قُلۡ هَلۡ
تَرَبَّصُونَ بِنَآ إِلَّآ إِحۡدَى ٱلۡحُسۡنَيَيۡنِۖ وَنَحۡنُ نَتَرَبَّصُ بِكُمۡ أَن يُصِيبَكُمُ ٱللَّهُ بِعَذَابٖ مِّنۡ
عِندِهِۦٓ أَوۡ بِأَيۡدِينَاۖ فَتَرَبَّصُوٓاْ إِنَّا مَعَكُم مُّتَرَبِّصُونَ ﴿٥٢﴾

**51-52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ለእኛ የጻፈልን ጥቅም እንጂ ሌላ አይነካንም። እርሱ ረዳታችን ነው። ምዕምናን በአላህ ላይ ብቻ ይመኩ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእኛ ላይ ከሁለቱ መልካሞች አንደኛዋን እንጂ ሌላን ትጠባበቃላችሁን? እኛም አላህ ከእርሱ በሆነው ቅጣት ወይም በእጆቻችን የሚያጠፋችሁ መሆኑን በእናንተ ላይ እንጠባበቃለን። እናንተም ተጠባበቁ። እኛም ከናንተው ጋር ተጠባባቂዎች ነንና በላቸው።

قُلۡ أَنفِقُواْ طَوۡعًا أَوۡ كَرۡهٗا لَّن يُتَقَبَّلَ مِنكُمۡ إِنَّكُمۡ كُنتُمۡ قَوۡمٗا فَٰسِقِينَ ﴿٥٣﴾ وَمَا مَنَعَهُمۡ
أَن تُقۡبَلَ مِنۡهُمۡ نَفَقَٰتُهُمۡ إِلَّآ أَنَّهُمۡ كَفَرُواْ بِٱللَّهِ وَبِرَسُولِهِۦ وَلَا يَأۡتُونَ ٱلصَّلَوٰةَ إِلَّا وَهُمۡ
كُسَالَىٰ وَلَا يُنفِقُونَ إِلَّا وَهُمۡ كَٰرِهُونَ ﴿٥٤﴾ فَلَا تُعۡجِبۡكَ أَمۡوَٰلُهُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُهُمۡۚ إِنَّمَا يُرِيدُ
ٱللَّهُ لِيُعَذِّبَهُم بِهَا فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَتَزۡهَقَ أَنفُسُهُمۡ وَهُمۡ كَٰفِرُونَ ﴿٥٥﴾

**53-55.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወዳችሁም ሆነ ጠልታችሁ ለግሱ። ከናንተ ተቀባይ የላችሁም። እናንተ አመፀኛ ህዝቦች ናችሁና በላቸው። ልግስናዎቻቸውን ከእነርሱ ተቀባይነት እንዳይኖራቸው ያደረገው እነርሱ በአላህና በመልዕክተኛው የካዱ፤ ሶላትንም ስልቹዎች ሆነው በስተቀር የማይሰግዱ* እነርሱም ጠይዎች ሆነው በስተቀር የማይሰጡ መሆናቸው እንጂ ሌላ ነገር አልከለከላቸውም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ገንዘቦቻቸውና ልጆቻቸው አይድነቁህ። አላህ የሚሻው በቅርቢቱ ህይወት በእነርሱ በገንዘቦቻቸውና በልጆቻቸው ሊቀጣቸው ነፍሶቻቸውም ከሓዲያን ሆነው ሊሞቱ ብቻ ነው።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (53) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ጀድ ብኑ ቀይስ የተባለው አስመሳዮች በተናገረው ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

✷ የአላህ መልዕክተኛ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል:- «መናፍቃን ላይ ከባድ የሆኑ ሶላቶች የፈጅርና የዒሻእ ሶላቶች ናቸው።

وَيَحۡلِفُونَ بِٱللَّهِ إِنَّهُمۡ لَمِنكُمۡ وَمَا هُم مِّنكُمۡ وَلَٰكِنَّهُمۡ قَوۡمٞ يَفۡرَقُونَ ٥٦ لَوۡ يَجِدُونَ مَلۡجَـًٔا
أَوۡ مَغَٰرَٰتٍ أَوۡ مُدَّخَلٗا لَّوَلَّوۡاْ إِلَيۡهِ وَهُمۡ يَجۡمَحُونَ ٥٧ وَمِنۡهُم مَّن يَلۡمِزُكَ فِي ٱلصَّدَقَٰتِ فَإِنۡ
أُعۡطُواْ مِنۡهَا رَضُواْ وَإِن لَّمۡ يُعۡطَوۡاْ مِنۡهَآ إِذَا هُمۡ يَسۡخَطُونَ ٥٨ وَلَوۡ أَنَّهُمۡ رَضُواْ مَآ ءَاتَىٰهُمُ ٱللَّهُ
وَرَسُولُهُۥ وَقَالُواْ حَسۡبُنَا ٱللَّهُ سَيُؤۡتِينَا ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦ وَرَسُولُهُۥٓ إِنَّآ إِلَى ٱللَّهِ رَٰغِبُونَ ٥٩

**56-59.** (ሙስሊሞች ሆይ!) እነርሱም በእርግጥ ከናንተ ጋር ለመሆናቸው በአላህ ይምላሉ። ግን ከናንተ ጋር አይደሉም። ይልቁንም እነርሱ አጋሪዎችን ያገኘው ነገር እንዳያገኛቸው የሚፈሩ ህዝቦች ናቸው። መናፍቃኖች መጠጊያን ቦታ ወይም መሸሸጊያ ዋሻዎችን ወይም መግቢያ ቀዳዳዎችን ባገኙ ኖሮ እነርሱ በፍጥነት ወደ እርሱ በሸሹ ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ መካከል በምጽዋቶች ክፍፍል ዙሪያ የሚዘልፉህ ሰዎች አሉ። ከእርሷም የሚሹትን ያህል ቢሰሰጡ ይደሰታሉ። ከእርሷ ምንም ካልተሰጣቸው ግን ያን ጊዜ ይጠላሉ። እነርሱም አላህና መልእክተኛው የሰጣቸውን በወደዱ፤ አላህ በቂያችን ነው አላህና መልዕክተኛው ከችሮታቸው በእርግጥ ይሰጠናል መልዕክተኛውም (ይሰጠናል) እኛ ወደ አላህ ከጃዮች ነን ባሉ ኖሮ (በተሻላቸው ነበር)።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (58) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ነብዩ (ﷺ) ምርኮን እያከፋፈሉ ሳሉ ዙልኹወይሲራህ የተባለ ሰው ይመጣና «አስተካክል» ይላቸዋል። እሳቸውም እኔ «ካላስተካከልኩኝ ማን ያስተካክላል» በማለት ሲመልሱለት ይህ አንቀፅ ወረደ። (ቡኻሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከ (49-59) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የጀድ ቢን ቀይስ የተባለው ከሃዲ በሰራው ወንጀል ምክንያት ቁርኣን እንዳጋለጠው፤
2. አስመሳዮችና ከሓዲያን ሙስሊሞችን የሚያስከፋ ክስተት ሲፈጠርና የሙስሊሞችን ልብ የሚያሳዝን ነገር ሲከሰት የሚደሰቱ መሆኑን፤
3. በአላህ ላይ ብቻ መመካት አስፈላጊና ወሳኝ ጉዳይ ስለመሆኑ፤
4. ሙዕሚኖች በጂሃድ ወቅት ከሁለት መልካም እድሎች ውስጥ አንዱን የማግኘት እድላቸው የተጠበቀ መሆኑን፤
5. የጠላትን ኃይል አንገት የሚያስደፋና የሚያስከፋ ቃላት መናገር የጠላትን ሞራል የሚሰባብር በመሆኑ ያለውን ጠቀሜታ፤

6. ለይዩልኝና ለይስሙልኝ የሚሰሩ ስራዎች በሙሉ ሌሎች መልካም ተግባራትን በሙሉ እንደሚበክሉና እንደሚያበላሹ፤ እንዲሁም ሽርክ በአላህ ማጋራት ደግሞ የመልካም ተግባርን ምንዳ የሚያሳጣና የስራውን ፋይዳ እንደሚያጠፋው፤
7. አመፀኛ የሚለው ቃል የክህደት አራማጅ ለሆኑ ሰዎች አንዱ መጠሪያ ስለ መሆኑ፤
8. በሰላት ላይ መናገር በአፈፃፀሙም ላይ መሳነፍ የተከለከለ መሆኑን፤
9. በውሸት መሀላ መደርደር የአስመሳዩች መለያ ባህሪይ ስለመሆኑ፤
10. ፍርሀት ከአስመሳዩች መገለጫ ባህሪያት አንዱ ስለ መሆኑ፤
11. ሙስሊሞችን ማንቋሸሽና ማነወር በልብ ውስጥ የስነ ምግባር ብልሹነት እንዳለ የሚያመለክት ስለ መሆኑ፤
12. አላህ አስመሳዩች የሚያራምዱትን የተጠላ ተግባር በመተው ወደ መልካም ስራዎች እንዲመለሱ ምክር ያስተላፈ ስለመሆኑ፤
13. አላህ ብቸኛና መመኪያችን፤ ብቸኛው ተስፋ የሚጣልበት ኃያል ጌታ እንደሆነ እንማራለን።

۞ إِنَّمَا ٱلصَّدَقَٰتُ لِلْفُقَرَآءِ وَٱلْمَسَٰكِينِ وَٱلْعَٰمِلِينَ عَلَيْهَا وَٱلْمُؤَلَّفَةِ قُلُوبُهُمْ وَفِى ٱلرِّقَابِ
وَٱلْغَٰرِمِينَ وَفِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱبْنِ ٱلسَّبِيلِ ۖ فَرِيضَةً مِّنَ ٱللَّهِ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ﴿٦٠﴾

**60.** ግዴታ ዘካን የሚከፈሉት ለድሆች፤ ለችግረኞች፤ በእርሷም ላይ ለሚሰሩ ሠራተኞች፤ ልቦቻቸው በኢስላም ለሚለማመዱት ወገኖች፤ ጫንቃዎችን ነጻ ለማውጣት ባለ እዳ ለሆኑት፤ ባሪያዎች በአላህ መንገድም✳ የሚሰሩና ስንቅ ላለቀበት መንገደኛ ብቻ ነው። ይህ ስርአት ከአላህ የተደነገገ ግዴታ ነው። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነውና።

✳ በአላህ መንገድ በሚለው ተደጋጋሚ ቃል ዙሪያ ያሉ ልዩነቶችን በተመለከተ እንደሌሎች ሰፋ አድርጎ መረጃዎችን በማጣቀስ ማስፈር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህን ፁሑፍ ለማዘጋጀት ወደድኩ። ጥሬ ትርጉሙ የአላህ መንገድ ማለት ሲሆን በቁርአን ውስጥ ከ 60 ጊዜ በላይ ተወስቷል። በተወሳበት ቦታ ሁሉ ራሱን የቻለ ትርጉም አለው? ወይስ አንድ አይነት ትርጉም ነው? በሚለው ዙሪያ ላይ ጠንካራ ክርክሮች በሚነሱበት ክርክሮች ላይ አሳማኝ ሆኖ የሚገኘው በተወሳበት ቦታ ሁሉ መልዕክቱ አንድ ሆኖ በስፋትና በጥበት ሊለያይ ይችላል። የሚለው ነው። ፊሰቢሊላህ በቁርአን ውስጥ የተወሳው በአንድ በኩል «ለእርሱ ተዋደቁ፤ በእርሱ ላይ መዋዕለ ነዋዮቻችሁን አፍስሱ» ለማለት ሲሆን፤ በሌላ በኩል ደግሞ «ከዚህ መንገድ እንቅፋት የሚሆኑ የአላህን መንገድ የሚጠሉና የሚያጣጥሉ» በማለት ነው። በሁለቱም አባባሎች ላይ ፊሰቢሉላህ የአላህ መንገድ የሚለው ኢስላም ኸይር ነገርሁሉን ማለት በመሆኑ ምንም አይነት ኺላፍ የለም። ክርክሩ ያው ሁል ጊዜ «በዚሁ በሰፊው ነው መተርጎም ያለበት ወይንስ እንዳመጣጡ ተስማሚ ለሆነው መልዕክት መወሰን አለበት» የሚል ነው።

1. «መወሰን የለበትም ሰፊውን መልዕክት ይዞ በየተወሳበት ቦታና አጋጣሚ የአላህን ፈቃድ የሚያሟሉ መልካም ነገሮችን ሁሉ እንደሚያጠቃልል መታየት አለበት» በማለት አቋማቸውን ያፀኑ በርካታ ዑለማዎች ናቸው። ይህን አባባል ከደጋፊ ሙፈሲሮችና ሙሐዲሶች መካከል ጀማሉዲን አልቃሲሚ፤ ኢብኑ ከሲር፤ መሃሲኑ ተዕዊል፤ ሲዲቅ ሐሰን ኻን፤ ሶንዓኒ፤ አል ሙባረክ ፉሪ፤ አል ካሳኒ፤ ሌሎችም ይህን አባባል ይቀበላሉ። ከዚህም በመነሳት የዘካ ገንዘብ ከጂሀድ ውጭ ለኸይር ስራዎች መስጠት ይቻላል። ይህ ማለት ለአስተማሪዎች፤ ለትምህርት ቤቶች ማስገንቢያና ማስተዳደሪያ፤ ለመስጊድ ግንባታና አስተዳደር ወቅፍ መስሪያ ወ. ዘ. ተ

መስጠት ይቻላል ይላሉ። እኔም የምቀበለውና የምደግፈው ይህኑ አባባል ነው። በተለይም በአሁኑ ጊዜ በግልፅ ጂሃድ ላይ የተሰማሩ ሰዎች በሌሉበትና በቀላሉ በማይገኙበት ጊዜ የፊሰቢሊላህ ድርሻ ቢያንስ በአፉቸው እንኳን መጥፎ ነገርን እየተዋጉ ያሉ አስተማሪዎች ይህን ሊያራብራሩ የሚችለውን መፅሐፍት ለማስፋፋት እንዲችሉ ማውጣት አማራጭ የሌለው ነው ብዬ አምናለሁ። ለዚህም ማስረጃ ካስፈለገ፡-

2. ኛው ራሱ ቃሉ የሚያሳየው ስለ ሆነ የሚያመላክተው መልዕክት መካከል በተወሰነ ጉዳይ ላይ ብቻ መወሰን ማስረጃ ስለሚያስፈልግና ለዚህም የሚሆን ግልፅ ማስረጃ ባለመኖሩ፤
3. ኛው የሐጅና የዑምራ ስራ ነብዩም (ﷺ) ሱሃቦች በዚሁ ፊሰቢሊላህ ውስጥ እንደሚካተት በመናገራቸው ነው።
4. ኛው መዝሀብ ደግሞ «እንደ አመጣጡ መተርጎም አለበት» የሚል ሲሆን ይህ በቁርኣን ፊሰቢሊላህ ጂሃድ ብቻ ነው የሚል ነው። ይህ አባባል ብዙ ዑለማዎችና ሙፊሲሮች የተጓዙበት ነው። ይህን አባባል የተቀበሉ ሰዎች ያቀረቡት ምክንያት በተለይም የዘካን አንቀፅ ሲሆን «ፊሰቢሊላህ» የሚለው በሰፊ ከተነገረው ጋር አይጣጣምም። ምክንያቱም አብረውት የተወሱት ሰባቱ ክፍሎች ራሳቸው በሰፊው ከታዩ በዚሁ ስር የሚጠቃለሉ በመሆናቸው ነው ይላሉ። ከተጠቃለሉ ደግሞ እንደገና መዘርዘሩ ምን ጥቅም አለው በሚል ተልካሻ ምክንያት ነው።

وَمِنْهُمُ ٱلَّذِينَ يُؤْذُونَ ٱلنَّبِيَّ وَيَقُولُونَ هُوَ أُذُنٌۚ قُلْ أُذُنُ خَيْرٍ لَّكُمْ يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَيُؤْمِنُ
لِلْمُؤْمِنِينَ وَرَحْمَةٌ لِّلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مِنكُمْۚ وَٱلَّذِينَ يُؤْذُونَ رَسُولَ ٱللَّهِ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٦١﴾
يَحْلِفُونَ بِٱللَّهِ لَكُمْ لِيُرْضُوكُمْ وَٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥٓ أَحَقُّ أَن يُرْضُوهُ إِن كَانُوا۟ مُؤْمِنِينَ ﴿٦٢﴾ أَلَمْ
يَعْلَمُوٓا۟ أَنَّهُۥ مَن يُحَادِدِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَأَنَّ لَهُۥ نَارَ جَهَنَّمَ خَٰلِدًا فِيهَاۚ ذَٰلِكَ ٱلْخِزْىُ ٱلْعَظِيمُ ﴿٦٣﴾

**61-63.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመናፍቃን መሐከል እነዚያ ነብዩን (ሙሐመድን) የሚያሰቃዩና እርሱ እኮ ወሬ ሰሚ ነው የሚሉ አሉ ቢሆንም ለእናንተ የበጎ ወሬ ሰሚ ነው። በአላህ ያምናል። ምዕመናንንም ያምናቸዋል። ከናንተ መካከል ለእነዚያ በአላህ ላመኑት ሰዎችም እዝነት ነው በላቸው። እነዚያ የአላህን መልዕክተኛ የሚያሰቃዩ ሰዎች ሁሉ ለነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። አላህንና መልዕክተኛውን ሊያስወድዱ ሲገባቸው እናንተን ሊያስወድዷችሁ ዘንድ በአላህ ይምሉላችኋል። አማኞች ከሆኑ (ግን አላህንና መልዕክተኛው ሊያስወድዱ ይገባቸዋል)። አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከር ሰው ሁሉ በውስጡ ዘውታሪ ሲሆን የተዘጋጀችለት የገሀነም እሳት መሆኑን አያውቁምን? ይህ ደግሞ ታላቅ ውርደት ነው።

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ (61) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ጃላስ፤ ረፋዕህ ወደዓህና ሌሎችም የአስመሳዮች ቡድን በነብዩ ላይ ለመባል የማይገቡ ቃላትን ይናገራሉ። ከመሀከላቸውም አንዱ «ይህ ነገር ወደ ሙሐመድ ይደርስና ችግር ይደርስብናል ብለን እንፈራለን» ሲል ጁላስ «የፈለግነውን እንናገራለን። ከዚያም እንሂድ። ያልነውን ይቀበለናል ሙሐመድ እኮ ወሬ አዳማጭ ነው» በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

*ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (62) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አሚር ቢን ቀይስ የተባለ ወጣት ሱሃቢ ባለበት አስመሳዮች ተሰብስበው «ሙሐመድ የሚናገረው ትክክል ከሆነ እኛ ከአህዮች ያነስን ነን ማለት ነው» ሲሉ አሚር ቢን ቀይ ተነስቶ በቁጣ «ነብዩ የሚሉት ሁሉ ትክክል ነው። እናንተም ከአህያ በታች ናችሁ» አላቸው። ወደ ነብዩም (ﷺ) ሄዶ ታሪኩን ተናገረ። ነብዩም ጠርተው ሲጠይቋቸው «አሚር ያለው ውሸት ነው» አሉና ማሉ። በዚህ ጊዜ አሚር «ውሸታሞቹ እነሱ ናቸው» በማለት ማለ። አስከትሎም «ጌታዬ ሆይ! ሳንነጣጠል እውነተኛውንንና ውሸታሙን ለይ» ብሎ ዱዓ አደረገ። ወዲያውኑ ይህ አንቀፅ ወረደ።*

يَحۡذَرُ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ أَن تُنَزَّلَ عَلَيۡهِمۡ سُورَةٞ تُنَبِّئُهُم بِمَا فِي قُلُوبِهِمۡۚ قُلِ ٱسۡتَهۡزِءُوٓاْ إِنَّ ٱللَّهَ
مُخۡرِجٞ مَّا تَحۡذَرُونَ ٦٤ وَلَئِن سَأَلۡتَهُمۡ لَيَقُولُنَّ إِنَّمَا كُنَّا نَخُوضُ وَنَلۡعَبُۚ قُلۡ أَبِٱللَّهِ وَءَايَٰتِهِۦ
وَرَسُولِهِۦ كُنتُمۡ تَسۡتَهۡزِءُونَ ٦٥ لَا تَعۡتَذِرُواْ قَدۡ كَفَرۡتُم بَعۡدَ إِيمَٰنِكُمۡۚ إِن نَّعۡفُ عَن
طَآئِفَةٖ مِّنكُمۡ نُعَذِّبۡ طَآئِفَةَۢ بِأَنَّهُمۡ كَانُواْ مُجۡرِمِينَ ٦٦ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ وَٱلۡمُنَٰفِقَٰتُ بَعۡضُهُم مِّنۢ
بَعۡضٖۚ يَأۡمُرُونَ بِٱلۡمُنكَرِ وَيَنۡهَوۡنَ عَنِ ٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَقۡبِضُونَ أَيۡدِيَهُمۡۚ نَسُواْ ٱللَّهَ فَنَسِيَهُمۡۚ
إِنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ هُمُ ٱلۡفَٰسِقُونَ ٦٧ وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ وَٱلۡمُنَٰفِقَٰتِ وَٱلۡكُفَّارَ نَارَ جَهَنَّمَ
خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ هِيَ حَسۡبُهُمۡۚ وَلَعَنَهُمُ ٱللَّهُۖ وَلَهُمۡ عَذَابٞ مُّقِيمٞ ٦٨

**64-68.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መናፍቃን በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ የሚነግራቸው ምእራፍ በእነርሱ ላይ መወረዱን ዘወትር ይፈራሉ። ቀልዱ። አላህ የምትፈሩትን ነገር ሁሉ ገላጭ ነው በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ብትጠይቃቸው እኛ የምንዘባርቅና የምንጫወት ሰዎች ብቻ ነበርን ይላሉ። በአላህና፤ በአናቅጹ በመልክተኛውም ላይ ትቀልዱ ነበራችሁን? በላቸው። አስመሳዮች ሆይ፣ አታመካኙ ከእምነታችሁ በኋላ በእርግጥ በአላህ ክዳችኋልና። ከናንተ አንዷን ቡድን ብንምር የሌላዋን ቡድን አባላት ግን ኃጢአተኞች በመሆናቸው እንቀጣለን። የወንድ መናፍቃንና የሴት መናፍቃን ከፊሎቻቸው የከፊሉ አካል ናቸው። በመጥፎ ነገር ያዛሉ። ከደግ ነገርም ይከለክላሉ። እጆቻቸውን ከልግስና ይሰበስባሉ። ለአላህ መታዘዝን ተዉ። ስለዚህ እርሱም ተዋቸው። መናፍቃን አመፀኞች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። መናፍቃንንና መናፍቃትን እንዲሁም ከሓዲያንን አላህ የገሀነምን እሳት በውስጧ ዘውታሪዎች ሲሆኑ ቃል ገብቶላቸዋል። እርሷ በቂያቸው ናት። አላህ ረግሟቸዋል። ለእነርሱም ዘውታሪ ቅጣት አለባቸው።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (64) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ አስመሳዮች «ዝንት አለም የሚያዋርደን ቁርአን ከሚወርድ መቶ ጅራፍ ብንገረፍ ይሻለን ነበር» በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (65) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በተቡክ ዘመቻ ጊዜ አንድ ሰው በአንድ ቦታ «እንደ እኛ አንባቢዎች ያለ ሆዳም፤ ዋሾ፤ በቅባታ ፈሪ አላየንም» ሲል ሌላ ሰው ተነስቶ ዋሸህ። አንተ አስመሳዮች ነህ። ይህን ጉዳይ ደግሞ ለነብዩ (ﷺ) እናገራለሁ አለ። ነብዩም (ﷺ) ተነገራቸው። ከዚያም የአስመሳዮችን አለቃዎች አስጠርተው ሲጠይቋቸው «እኛ እኮ ስንቀልድ» ስላሉ ነው ይህ ቁርአናዊ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

كَٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ كَانُوٓاْ أَشَدَّ مِنكُمۡ قُوَّةٗ وَأَكۡثَرَ أَمۡوَٰلٗا وَأَوۡلَٰدٗا فَٱسۡتَمۡتَعُواْ بِخَلَٰقِهِمۡ فَٱسۡتَمۡتَعۡتُم بِخَلَٰقِكُمۡ كَمَا ٱسۡتَمۡتَعَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُم بِخَلَٰقِهِمۡ وَخُضۡتُمۡ كَٱلَّذِي خَاضُوٓاْۚ أُوْلَٰٓئِكَ حَبِطَتۡ أَعۡمَٰلُهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ٦٩

**69.** (አስመሳዮች ሆይ)፤ ተግባራችሁ ልክ እንደእነዚያ ከናንተ በፊት እንደነበሩት ህዝቦች ነው። ከናንተ ይበልጥ በሃይል የበረቱ በገንዘብና በልጆችም ከናንተ ይበልጥ የበዙ ነበሩ። በእድላቸው ተጠቀሙ። እንደ ተጠቀሙ ሁሉ እናንተም በእድላችሁ ተጠቀማችሁ። እንደእነዚያም እንደ ዘባረቁት ዘባረቃችሁ። እነዚያ ስራዎቻቸው በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ተበላሹ። ከሳሪዎቹ ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው።

أَلَمۡ يَأۡتِهِمۡ نَبَأُ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ قَوۡمِ نُوحٖ وَعَادٖ وَثَمُودَ وَقَوۡمِ إِبۡرَٰهِيمَ وَأَصۡحَٰبِ مَدۡيَنَ وَٱلۡمُؤۡتَفِكَٰتِۚ أَتَتۡهُمۡ رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِۖ فَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيَظۡلِمَهُمۡ وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ يَظۡلِمُونَ ٧٠

**70.** የእነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት የነብዩ ኑህ፣ የዓድ፣ የሰሙድ፣ የነብዩ ኢብራሂም ህዝቦች፤ የመድየን ባለቤቶችና የተገልባጮቹም ከተሞች ታሪክ አልመጣላቸውምን? መልዕክተኞቻቸው ግልፅ ተዐምራትን አመጡላቸው። አላህ የሚበድላቸው አልነበረም። ግን በራሳቸው ነፍሶቻቸውን የሚበድሉ ነበሩ።

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (60-70) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ዘካ መከፈል አቅሙ በቻለ ሙስሊም ላይ በሙሉ የተጣለ ኢስላማዊ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
2. ነብዩን (ﷺ) አዛ ማድረግ (ማስቸገር) መከልከሉን፤
3. ነብዩን (ﷺ) የሚያስቸግሩ ሰዎች በሙሉ ከአላህ ቅጣት እንደሚያገኛቸው፤

4. ከሓዲያን ውሸታሞችና ፈሪዎች እንደሆኑ፤
5. የአላህን ውዴታ የሚያስገኙ መልካም ተግባራትን የማብዛት አስፈላጊነት፤
6. አላህንና ነብዩን (ﷺ) የሚከራከሩ ሰዎች በአላህ ዘንድ የሚጠብቃቸው ቅጣት ክብደት፤
7. የአስመሳዩች ሕይወት ምን አይነት ይዘት እንዳለውና ምን እንደሚመስል፤
8. አላህ ባወረዳቸው ቁርአናዊ አናቅፅ እንዲሁም በመልዕክተኛው ሙሐመድ (ﷺ) ላይ ለቀልድም ቢሆን እንኳን ያፌዘና ያላገጠ ከኢስላም የሚወጣ ስለመሆኑ፤
9. ካመነ በኋላ እምነቱን ረግጦ ወደ ክህደት የገባ ሰው ንሰሃ ተቀባይት የሌለው ስለ መሆኑ፤
10. አላህ ቅጣቴን እፈፅምባቸዋለሁ ያለውን የዛቻ ቃል መፈፀሙን፤
11. የመናፍቃን የልብ በሽታ አንዱ መሆኑን የተግባራቸው መመሳሰል እንደሚያረጋግጥ፤
12. ምግባረ ብልሹነት እንዲስፋፋ መልካም ነገሮች እንዲከስሙ መጣር የአስመሳዮች ባህሪይ ስለ መሆኑ፤
13. በገንዘብና በልጅ መመካት ሐቅን ላለመቀበል የሚዳርግ አስከፊ ባህሪይ ስለመሆኑ፤
14. ከቀደምት ሰዎች ያለፈ ታሪክ ትምህርት መውሰድ ለዛሬውና ለነገው ሕይወት የሚጠቅም መሆኑን በመገንዘብ ካለፈ ታሪክ መማር እንደሚገባ እንማራለን።

وَٱلۡمُؤۡمِنُونَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتُ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلِيَآءُ بَعۡضٖۚ يَأۡمُرُونَ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَيَنۡهَوۡنَ
عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَيُقِيمُونَ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَيُطِيعُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓۚ
أُوْلَٰٓئِكَ سَيَرۡحَمُهُمُ ٱللَّهُۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٞ ٧١

**71.** የወንድ አማኞችና የሴት አማኞች ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው። በደግ ነገር ያዝዛሉ። ከክፉም ነገር ይከለክላሉ። ሶላትን ይሰግዳሉ። ዘካን ይሰጣሉ። አላህንና መልዕክተኛውን ይታዘዛሉ። እነዚያን አላህ በእርግጥ ያዝንላቸዋል። አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَا وَمَسَٰكِنَ
طَيِّبَةٗ فِي جَنَّٰتِ عَدۡنٖۚ وَرِضۡوَٰنٞ مِّنَ ٱللَّهِ أَكۡبَرُۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ٧٢

**72.** አላህ የወንድ አማኞችንና የሴት አማኞችን ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ በመኖሪያ ገነቶችም ውስጥ መልካም መኖሪያ ቤቶችን ቃል ገብቶላቸዋል። ከአላህ የሆነ ውዴታ ደግሞ ከሁሉ የበለጠ ነው። ይህ እርሱ ታላቅ ዕድል ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ جَٰهِدِ ٱلْكُفَّارَ وَٱلْمُنَٰفِقِينَ وَٱغْلُظْ عَلَيْهِمْ ۚ وَمَأْوَىٰهُمْ جَهَنَّمُ ۖ
وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿٧٣﴾ يَحْلِفُونَ بِٱللَّهِ مَا قَالُوا۟ وَلَقَدْ قَالُوا۟ كَلِمَةَ ٱلْكُفْرِ وَكَفَرُوا۟ بَعْدَ
إِسْلَٰمِهِمْ وَهَمُّوا۟ بِمَا لَمْ يَنَالُوا۟ ۚ وَمَا نَقَمُوٓا۟ إِلَّآ أَنْ أَغْنَىٰهُمُ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ مِن فَضْلِهِۦ ۚ
فَإِن يَتُوبُوا۟ يَكُ خَيْرًا لَّهُمْ ۖ وَإِن يَتَوَلَّوْا۟ يُعَذِّبْهُمُ ٱللَّهُ عَذَابًا أَلِيمًا فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْءَاخِرَةِ ۚ
وَمَا لَهُمْ فِى ٱلْأَرْضِ مِن وَلِىٍّ وَلَا نَصِيرٍ ﴿٧٤﴾

**73-74.** አንተ ነብዩ ሆይ፣ ከሓዲያንንና መናፍቃንን ታገል። በእነርሱ ላይም ብርቱ ሁንባቸው። መኖሪያቸውም ገሀነም ናት። መመለሻይቱም በጣም ከፋች። ምንም ያላሉ ለመሆናቸው በአላህ ይምላሉ። ግን የክህደትን ቃል በእርግጥ አሉ። ከእስልምናቸውም በኋላ ካዱ። ያላገኙትንም ነገር አሰቡ። አላህና መልዕክተኛው ከችሮታው ያከበራቸው መሆኑን እንጂ ሌላን አልጠሉም። ቢፀፀቱም ለእነርሱ የተሻለ ይሆናል። ቢሸሹ አላህ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም አሳማሚን ቅጣት ይቀጣቸዋል። ለእነርሱም በምድር ውስጥ ምንም ወዳጅና ረዳት የላቸውም።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (74) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
ከተቡክ ዘመቻ ከቀሩት መካከል ጀላስ አቡ ሱወይድ አንዱ ነበር። ይህ ሰው የሚለው ትክክል ከሆነ እኛ ከአህያ የባሰን መጥፎዎች ነን ማለት ነው» ብሎ ስለተናገረና ዑመይር ቢን ሰኢድ ይህን ጉዳይ ለነብዩ (ﷺ) ደረሰ ሲጠይቅ አላልኩም ብሎ በመማሉ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ሱዩጢ)

۞ وَمِنْهُم مَّنْ عَٰهَدَ ٱللَّهَ لَئِنْ ءَاتَىٰنَا مِن فَضْلِهِۦ لَنَصَّدَّقَنَّ وَلَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٧٥﴾
فَلَمَّآ ءَاتَىٰهُم مِّن فَضْلِهِۦ بَخِلُوا۟ بِهِۦ وَتَوَلَّوا۟ وَّهُم مُّعْرِضُونَ ﴿٧٦﴾ فَأَعْقَبَهُمْ نِفَاقًا فِى قُلُوبِهِمْ
إِلَىٰ يَوْمِ يَلْقَوْنَهُۥ بِمَآ أَخْلَفُوا۟ ٱللَّهَ مَا وَعَدُوهُ وَبِمَا كَانُوا۟ يَكْذِبُونَ ﴿٧٧﴾ أَلَمْ يَعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ
يَعْلَمُ سِرَّهُمْ وَنَجْوَىٰهُمْ وَأَنَّ ٱللَّهَ عَلَّٰمُ ٱلْغُيُوبِ ﴿٧٨﴾

**75-78.** ከእነርሱ መካከል አላህን ከችሮታው ቢሰጠን በእርግጥ እንመፀውታለን። ከመልካሞችም እንሆናለን ሲል ቃል የገባ አለ። ከዚያ ከችሮታው በሰጣቸው ጊዜ ሰሰቱ። እነርሱ ቃል ኪዳናቸውን የተው ሆነውም ዞሩ። ለአላህ ቃል የገቡትን በማፍረሳቸውና ይዋሹትም በነበሩት ውሸት ምክንያት እስከሚገናኙት ቀን ድረስ ንፍቅናን አስከተላቸው። (አስመሳዮችን) አላህ ምስጢራቸውንና ውይይታቸውን የሚያውቅ መሆኑንና አላህ ሩቅ ነገሮችን ሁሉ በጣም ዐዋቂ መሆኑን አያውቁምን?

ٱلَّذِينَ يَلْمِزُونَ ٱلْمُطَّوِّعِينَ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ فِى ٱلصَّدَقَٰتِ وَٱلَّذِينَ لَا يَجِدُونَ إِلَّا جُهْدَهُمْ فَيَسْخَرُونَ مِنْهُمْ سَخِرَ ٱللَّهُ مِنْهُمْ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٧٩﴾ ٱسْتَغْفِرْ لَهُمْ أَوْ لَا تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ إِن تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ سَبْعِينَ مَرَّةً فَلَن يَغْفِرَ ٱللَّهُ لَهُمْ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ كَفَرُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱللَّهُ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٨٠﴾

**79-80.** እነዚያ ከምዕምናን በምጽዋቶች ፈቃደኛ የሆኑትን እነዚያንም የችሎታቸውን ያክል እንጂ የማያገኙትን ሰዎች የሚያነውሩና በእነርሱ የሚሳለቁ ሰዎች ሁሉ አላህ ከእነርሱ ይሳለቅባቸዋል። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነርሱ ምሕረትን ብትለምንላቸውም ወይም ባትለምንላቸው ሁሉም እኩል ነው። ለእነርሱ ሰባ ጊዜ ምህረትን ብትለምንላቸው እንኳን አላህ በፍፁም አይምራቸውም። ምክንያቱም እነርሱ በአላህና በመልዕክተኛው ክደዋልና። አላህ አመፀኞች ህዝቦችን አያቀናም።

*ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (79) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የሰደቃ አንቀፅ በወረደ ጊዜ አንዳንዶች ብዙ ገንዘብና እህል እያመጡ ሲሰጡ አስመሳዮች «ይህ እዩልኝ ባይነት ነው አሉ። ሌላው ደግሞ አንድ ድሃ አንድ ቁና ታህል ሲያመጣ «አላህ ከዚህ ድሃ ሰደቃ የተብቃቃ ነው» በማለት በማፌዛቸውና በማንጓጠጣቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)*

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (71-80) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

1. *የምዕመናን ባህሪይ ምን እንደሚመስል፤*
2. *የአላህን ውዴታ ከሁሉም ነገር የተሻለና የበለጠ ስለ መሆኑ፤*
3. *ኢስላምን ተቀብለው ከኖሩ በኋላ ወደ ክህደት የሚመለሱ ሰዎች የሚወሰድባቸው ምድራዊ ቅጣት፤*
4. *ተውባህ ያለፉትን ወንጀሎች በሙሉ የሚያሰርዝና ምህረት የሚያስገኝ መሆኑን፤*
5. *በክህደት ላይ እያሉ ሞትን የቀመሱ ሰዎች የሚጠብቃቸው ቅጣት አሰቃቂነት፤*
6. *ቃል ምንጊዜም የሚጠየቁበት እዳ መሆኑን፤*
7. *የገቡትን ቃል መፈፀም ኢስላማዊ ግድ፝ጃ መሆኑን፤*
8. *ንፉግነት በኢስላም የተወገዘ ተግባር ስለመሆኑ፤*
9. *ጥፋት በየጊዜው ካልታረመ ሌላ ጥፋት እንደሚያስከትል መገንዘብ እንደሚገባ፤*
10. *መጥፎ ሰዎችን መውቀስና ተግባራቸውንም ማውገዝ ብልሹነት በምድር ላይ እንዳይስፋፋ የሚያደርግ መሆኑን በማወቅ መጥፎ ሰዎችንና ድርጊታቸውን ማውገዝ፤ እንደሚገባ፤*
11. *አንድን አማኝ በአሽሙር መስደብ የተከለከለ ስለ መሆኑና በሙዕሚኖች ማላገጥ እንደዚሁ የተከለከለ እንደሆነ፤*
12. *አላህ ለቅን አገልጋይ ባሪያዎቹ ውዴታና እንክብካቤውን የማያቋርጥ ለእነሱም ቀና የሆነ መጎዳታቸውንም የማይፈለግ ስለ መሆኑ፤*
13. *በክህደት ላይ ሳለ ለሞተ ሰው የአላህን ምህረት መጠየቅ የማይቻል መሆኑን፤*
14. *በወንጀል ተግባራት ላይ ዘወታሪ መሆንና በኃጢአት መዘፈቅ የመመራትን በር የሚያጠብ ስለመሆኑ እንማራለን።*

فَرِحَ ٱلْمُخَلَّفُونَ بِمَقْعَدِهِمْ خِلَٰفَ رَسُولِ ٱللَّهِ وَكَرِهُوٓا۟ أَن يُجَٰهِدُوا۟ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْ
فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَقَالُوا۟ لَا تَنفِرُوا۟ فِى ٱلْحَرِّ ۗ قُلْ نَارُ جَهَنَّمَ أَشَدُّ حَرًّا ۚ لَّوْ كَانُوا۟ يَفْقَهُونَ ﴿٨١﴾
فَلْيَضْحَكُوا۟ قَلِيلًا وَلْيَبْكُوا۟ كَثِيرًا جَزَآءًۢ بِمَا كَانُوا۟ يَكْسِبُونَ ﴿٨٢﴾ فَإِن رَّجَعَكَ ٱللَّهُ إِلَىٰ
طَآئِفَةٍ مِّنْهُمْ فَٱسْتَـْٔذَنُوكَ لِلْخُرُوجِ فَقُل لَّن تَخْرُجُوا۟ مَعِىَ أَبَدًا وَلَن تُقَٰتِلُوا۟ مَعِىَ عَدُوًّا ۖ
إِنَّكُمْ رَضِيتُم بِٱلْقُعُودِ أَوَّلَ مَرَّةٍ فَٱقْعُدُوا۟ مَعَ ٱلْخَٰلِفِينَ ﴿٨٣﴾ وَلَا تُصَلِّ عَلَىٰٓ أَحَدٍ مِّنْهُم
مَّاتَ أَبَدًا وَلَا تَقُمْ عَلَىٰ قَبْرِهِۦٓ ۖ إِنَّهُمْ كَفَرُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَمَاتُوا۟ وَهُمْ فَٰسِقُونَ ﴿٨٤﴾

**81-84.** እነዚያ ከዘመቻ የቀሩት ሰዎች ከአላህ መልዕክተኛ በኋላ ተገንጥለው በመቀመጣቸው ተደሰቱ። በአላህ መንገድ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው መታገልን ጠሉ። ለሌሎችም በሐሩር አትሂዱ አሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የገሀነም እሳት ትኩሳት በጣም ከዚህ የበረታ ነው በላቸው። እናም የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ ከዘመቻው አይቀሩም ነበር። (አስመሳዮች) ጥቂት ጊዜን ይሳቁ። ይሠሩት በነበሩት እኩይ ተግባር ምክንያት ዋጋ ብዙ ጊዜ ያለቅሳሉና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ መካከል ወደ ሆነችው ቡድን አላህ በሰላም ቢመልስህና ከአንተ ጋር ዘመቻ ለመውጣት ቢያስፈቅዱህ ከእኔ ጋር በፍፁም አትወጡም። ከእኔም ጋር ጠላትን አትዋጉም። እናንተ በመጀመሪያ ጊዜ መቀመጥን ወዳችኋልና። ይልቁንም ከተቀማጮች ጋር ተቀመጡ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ መካከል በሞተ በአንዱም ሰው ላይ ቢሆን ፈጽሞ አትስገድ። በመቃብሩም ላይ አትቁም። እነርሱ በአላህና በመልዕክተኛው ክደዋልና። አመፀኞችም ሆነው ሞተዋልና።

وَلَا تُعْجِبْكَ أَمْوَٰلُهُمْ وَأَوْلَٰدُهُمْ ۚ إِنَّمَا يُرِيدُ ٱللَّهُ أَن يُعَذِّبَهُم بِهَا فِى ٱلدُّنْيَا وَتَزْهَقَ أَنفُسُهُمْ
وَهُمْ كَٰفِرُونَ ﴿٨٥﴾ وَإِذَآ أُنزِلَتْ سُورَةٌ أَنْ ءَامِنُوا۟ بِٱللَّهِ وَجَٰهِدُوا۟ مَعَ رَسُولِهِ ٱسْتَـْٔذَنَكَ
أُو۟لُوا۟ ٱلطَّوْلِ مِنْهُمْ وَقَالُوا۟ ذَرْنَا نَكُن مَّعَ ٱلْقَٰعِدِينَ ﴿٨٦﴾ رَضُوا۟ بِأَن يَكُونُوا۟ مَعَ ٱلْخَوَالِفِ
وَطُبِعَ عَلَىٰ قُلُوبِهِمْ فَهُمْ لَا يَفْقَهُونَ ﴿٨٧﴾

**85-87.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ገንዘቦቻቸውና ልጆቻቸው አይድነቁህ። አላህ የሚፈልገው በቅርቢቱ ዓለም በገንዘቦቻቸውና በልጆቻቸው ሊቀጣቸውና ከሓዲያንም ሆነው ነፍሶቻቸው እንዲወጡ ሊያደርግ ብቻ

ነውና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ እመኑ። ከመልዕክተኛው ጋር ሆናችሁ ታገሉ በማለት የቁርኣን ምእራፍ በተወረደ ጊዜ ከእነርሱ የሰፊ ሀብት ባለቤቶች የሆኑት ሰዎች ለመቅረት ፈቃድ ይጠይቁሃል። ከተቀማጮቹ ጋር እንሁን ተወን ይሉሃል። በቤት ከሚቀሩት ወገኖች ጋር መሆናቸውን ወደዱ። በልቦቻቸውም ላይ ዝገት ታተመባቸው። ስለዚህ እነርሱ አያውቁም።

لَٰكِنِ ٱلرَّسُولُ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَعَهُۥ جَٰهَدُواْ بِأَمْوَٰلِهِمْ وَأَنفُسِهِمْۚ وَأُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلْخَيْرَٰتُۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٨٨﴾ أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ ذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴿٨٩﴾

**88-89.** ግን መልዕክተኛውና ከእርሱ ጋር ያመኑት ሰዎች በገንዘቦቻቸውም በነፍሶቻቸውም ታገሉ። እነዚያም መልካሞች ሁሉ ለእነርሱ ብቻ የተዘጋጁ ናቸው። እነዚያም እነርሱ ምኞታቸውን ያገኙ ናቸው። አላህ ለእነርሱ በሥራቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶችን በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ አዘጋጅቶላቸዋል። ይህ ታላቅ እድል ነው።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከ (84-89) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የአስመሳዮች አለቃ የነበረው አብደላህ ቢን ኡበይ በሞተ ዕለት የእርሱ ልጅ አብደላ ወደ ነብዩ (ﷺ) ዘንድ መጣና ቀሚሣቸውን እንዲሰጡትና አባቱ እንዲገነዝበት ጠየቃቸው። እርሳቸውም ቀሚሣቸውን ሰጡትና ተገነዘበት። በመቀጠልም የጀናዛ ሠላት እንዲሰግዱበት ጠየቃቸው። ሊሰግዱበት ሲሉ ኡመር «እንዴት በአላህ ጠላት ላይ? በዚህ ቀን እንዲህ አለ፤ በዚህ ቀን እንዲህ አለ፤ እያሉ እንዴት ይሰግዳሉ?» ሲሉ ጠየቋቸው። ነብዩም (ﷺ) ፈገግ በማለት ካዳመጡ በኋላ «ዑመር ተወኝ እኔ ምርጫ ነው የተሰጠኝ እናም እኔም በእርሱ ላይ መስገድንና ምህረትን መለመንን መርጫለሁ። በርግጥም ምህረትን ብትለምንላቸውም ባትለምንላቸውም ሰባ ጊዜ ብትለምንላቸውም እንኳን አይማሩም ተብያለሁ። እኔ ግን የሚማር ከሆነ ከሠባ ጊዜ በላይ ለርሱ ምህረትን እጠይቃለሁ» ሲሉ ተናገሩና ሠገዱበት። ከዚያም ጀናዛውን አጅበው በቀብሩ ላይ ተገኙና ጥቂት እንደቆሙ አላህ ይህን አንቀፅ አወረደና ምህረትን ለአላህ ጠላቶች መለመን የተከለከለ መሆኑን በይፋ አወጀ። (ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ጦበሪ፤ ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَجَآءَ ٱلْمُعَذِّرُونَ مِنَ ٱلْأَعْرَابِ لِيُؤْذَنَ لَهُمْ وَقَعَدَ ٱلَّذِينَ كَذَبُواْ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥۚ سَيُصِيبُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنْهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٩٠﴾

**90.** ከአረብ ዘላኖች (ከአረብ አርብቶ አደሮች) መካከል ይቅርታ ፈላጊዎቹ እንዲፈቀድላቸው መጡ። እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን ያስተባበሉት ግን ተቀመጡ። እነዚያን በአላህ የካዱት ሰዎች አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ይነካቸዋል (ያገኛቸዋል)።

لَّيۡسَ عَلَى ٱلضُّعَفَآءِ وَلَا عَلَى ٱلۡمَرۡضَىٰ وَلَا عَلَى ٱلَّذِينَ لَا يَجِدُونَ مَا يُنفِقُونَ حَرَجٌ إِذَا
نَصَحُواْ لِلَّهِ وَرَسُولِهِۦۚ مَا عَلَى ٱلۡمُحۡسِنِينَ مِن سَبِيلٖۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٩١﴾

**91.** በደካሞች ላይ፣ በበሽተኞችም ላይ፣ በእነዚያም ለስንቅና ለትጥቅ የሚያወጡት ገንዘብ በማያገኙት ላይ ለአላህና ለመልዕክተኛው ፍፁም* ታዛዦች ከሆኑ ወደ ዘመቻ ባይወጡም ኃጢአት የለባቸውም። በበጎ አድራጊዎች ላይ ምንም የመወቀሻ መንገድ የለባቸውም። አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና።

✴ «ነሲሐ» የሚለው የአረብኛ ቃል የተለያዩ ትርጉሞች እንዳሉት ይታወቃል። ከእነዚህም ውስጥ፤ ፍፁምነት፤ ምክር፤ ታማኝነት» የሚሉት ትርጓሜዎች ይገኙበታል። እዚህ ላይ የተሻለው ፍፁምነት ወይም ታማኝነት የሚለው ትርጉም ነው። ተሚም ኢኢብኑ አውስ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ እንዲህ በማለት ነገሩን፡- «ሃይማኖተኝነት ታማኝነት (ነሲሐ) ነው አሉ። (እኛም) ለማን? አልናቸው። (እርሳቸም) ለአላህና ለመፅሐፍ፤ ለመልዕክተኛው፤ ለሙስሊሞች መሪዎችና ለህዝበ ሙስሊም ነው አሉን።»

وَلَا عَلَى ٱلَّذِينَ إِذَا مَآ أَتَوۡكَ لِتَحۡمِلَهُمۡ قُلۡتَ لَآ أَجِدُ مَآ أَحۡمِلُكُمۡ عَلَيۡهِ تَوَلَّواْ وَّأَعۡيُنُهُمۡ
تَفِيضُ مِنَ ٱلدَّمۡعِ حَزَنًا أَلَّا يَجِدُواْ مَا يُنفِقُونَ ﴿٩٢﴾ ۞إِنَّمَا ٱلسَّبِيلُ عَلَى ٱلَّذِينَ يَسۡتَـٔۡذِنُونَكَ
وَهُمۡ أَغۡنِيَآءُۚ رَضُواْ بِأَن يَكُونُواْ مَعَ ٱلۡخَوَالِفِ وَطَبَعَ ٱللَّهُ عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ فَهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٩٣﴾

**92-93.** በነዚያም መጓጓዣ ፈልገው ወደ አንተ በመጡ ጊዜ እናንተን የምጭንበት (አጋሰስ) አላገኘም ያልካቸው ስትሆን የሚያወጡት ገንዘብ ባለማግኘታቸው ለማዘናቸው ዓይኖቻቸው እንባን እያፈሰሱ በዞሩት ላይ (ምንም ወቀሳ የለባቸውም)።*1 (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሚወቀሱት እነዚያ ባለፀጋዎች ሆነው ሳሉ ለመቅረት ፈቃድ በሚጠይቁህ ሰዎች ብቻ ናቸው።*2 ከቀሪዎቹ ጋር መሆናቸውን ወደዱ። አላህ በልቦቻቸው ላይ አተመባቸው። ስለዚህ እነርሱ አያውቁም።

✴1 እንኳን ሊወቀሱ በጦርነቱም ላይ እንደተሳተፉ ተቆጥሮላቸዋል። ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከመካ በድል መከፈት በኋላ ስደት የለም። ግና ጂሃድና «ኒያህ» ምንጊዜም ይኖራሉ። ለጂሃድ እንድትዘምቱ በምትጠየቁበት ጊዜ ዝመቱ።» ብለዋል። አቢ ዐብደላህ ብኑ ጃቢር ዐብደላህ አል. አንሷሪይ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡- በአንድ ዘመቻ ላይ ነብዩ (ﷺ) ጋር ነበርን። እንዲህ አሉ፡- «መዲና ውስጥ በሽታ ከዘመቻ ያስቀራቸው ሰዎች አሉ። መንገድን አልሄዳችሁም፤ ሸለቆንም አላቋረጣችሁም ከናንተ ጋር ቢሆኑ እንጂ።»

✴2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከነብያት መካከል አንዱ ጦርነት ለማድረግ ተነሳ ለሕዝቦቹም «ከናንተ መካከል አንዲት ሴትን አግብቶ ከእርሷ ጋር ለማደር እየፈለገ ይህን ፍላጎቱን ሳይፈፅም የቀረ፤ ቤት ከሰራ በኋላ ጣሪያውን ሳይሰራ የቀረና ሴት ፍየል ወይም ግመል ገዝቶ መውለጃቸውን የሚጠብቅ ሰው አይከተለኝ» አለ። ልክ የዐስር ሶላት ወቅት ላይ ወይም ለዚህ ወቅት ቀረብ ብሎ እዚያ መንደር ደረሰና ለፀሐይ እንዲህ አላት «ፀሐይ ሆይ! አንቺም

የታዘዝሽ ነሽ እኔም የታዘዝኩን ነኝ። ጌታዬ ሆይ! በኛ ላይ እሷን ያዝልኝ» ሰዎቹ በጠላቶቻቸው ላይ ድል እስከሚቀዳጁ ድረስ ከመግባት ታገደች። የነብዩ ተከታዮች ድልን ከተቀዳጁ በኋላ የምርኮ ንብረቶችን በአንድነት ሰበሰቡ። እሳትም ይህን የምርኮ ንብረት ለማቃጠል መጣች። ነገር ግን አላቃጠለችውም። ያም ነብይ «ከናንተ መካከል አንዱ ከምርኮ ንብረት ሰርቋል። ማለት ነው ስለዚህ እያንዳንዱ ጎሳ እጇን በመጨበጥ ቃል ኪዳን ይፈፅም» አለ። ከጎሳዎቹ መካከልም የአንድ ሰው እጅ ከነብዩ እጅ ጋር ተጣበቀ ነብዩም «ስርቆቱ የተፈፀመው ከእናንተ ጎሳ ነው። ስለዚህ ሁሉም የጎሳ አባላት እጇን በመጨበጥ ቃኪዳን ይፈፅምልኝ አሉ። የሁለት ወይም የሶስት ሰዎች እጆች ከእጆቹ ጋር ተጣበቁ።«እናንተ ስርቆት ፈፅማችኋል» አላቸው፤ እነርሱም የከብት ጭንቅላት የሚያህል ወርቅ አመጡና አስቀመጡ። ከዚያም እሳት መጣችና አቃጠለችው። ከዚያ በኋላ ለእኛ የምርኮ ንብረትን አላህ ፈቀደልን። ደካማ በመሆናችንም አላህ የምርኮ ንብረትን ፈቀደልን።»

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ ከ (91-92) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- በተቡክ ዘመቻ ዕለት ነብዩ በዘመቻው ላይ እንዲሳተፉ ለሙስሊሞች ቅስቀሳ ሲያደርጉ ቁጥራቸው ከሰባት የማያንሱ በኑሮ ችግር የነበረባቸው ሙስሊሞች ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ከእርስዎ ጋር እንድንዘምት ጥሪ አድርጎልናል። እኛ ደግሞ መጓጓዣ፤ ስንቅና ትጥቅ የለንም። ከዚያም ከዚህም ብለው እርሶ ያመቻቹልን» አሏቸው። የአላህ መልዕክተኛም ደስ ይለኝ ነበር። ነገር ግን ይህን ማሟላት አልችልም አላገኘሁላችሁም» በማለት መለሱላቸው በእንባ እየተራጩ በሀዘን በተመለሱት ሰዎች ምክንያት ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ጦበሪ፤ ኢብኑ ከሲር፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (81-92) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ በወንጀል ስራ ደስተኛ እንደሆነ አስመስሎ ማቅረብ አልያም ማሰብ የአስመሳይነት ምልክት ስለመሆኑ፤
2. ሳቅ ማብዛት አላማን የሚያስትና የቧልት ሰው የሚያደርግ በመሆኑ የተጠላ ስለመሆኑ፤
3. ዒባዳን እያወቁ ችላ ማለትና መተው ለወደፊቱም ዒባዳውን ለመስራት የሚያስችል ኃይል ወይም የአላህን እገዛ እንደሚያስከለክል፤
4. በከሃዲ ላይ ሶላተል ጀናዛ መስገድ በአኼራ ሕይወቱ ላይ የሚያመጣው አንዳችም ለውጥ እንደሌለና መስገዱም የተከለከለ ስለመሆኑ፤
5. የከሃዲን አስክሬን በኢስላማዊ ስርዓት ማጠብም ሆነ መገነዝ ወይም መቅበር ለእርሱም ፀሎት ማድረግና የአላህን ምህረት መጠየቅ ክልል ስለመሆኑ፤
6. በፅኑ ወንጀለኞች ላይ ሶላተል ጀናዛ መስገድ የተከለከለ ስለመሆኑ፤
7. ከሓዲያንን አኗኗር፤ የእድገት ደረጃና አጠቃላይ ሁኔታ ማድነቅ የተከለከለ ስለመሆኑ፤
8. ቁርኣንና ሀዲስ የህግ ምንጭ የሆኑና የሙስሊሞች የሕይወት መመሪያ የተሟሉ መፅሐፍት እንደሆኑ፤
9. ለአንገብጋቢ ጉዳይ ከጂሃድ ግንባር ለመቅረት ከሙስሊሙ መሪ ዘንድ በመቅረብ ፈቃድ መጠየቅ የሚቻል ስለመሆኑ፤ ሆኖም ከጂሃድ ፍልሚያ ለመቅረት ግን የአሚሩን ፈቃድ ማግኘት ግዴታ ስለመሆኑ፤
10. ሙሃጂሮችና አንሷሮች በመባል የሚጠሩት በማይናወጥ መሰረት ላይ የተገነባ እምነት እንደነበራቸው፤
11. ነብዩ (ﷺ) ለሰዎች በሙሉ አክብሮትን የሚሰጡ መልካም ስነ. ምግባርና የተሟላ ስብዕና የነበራቸው ታላቅ ተምሳሌት የነበሩ ነብይ እንደነበሩ እንማራለን።

يَعۡتَذِرُونَ إِلَيۡكُمۡ إِذَا رَجَعۡتُمۡ إِلَيۡهِمۡۚ قُل لَّا تَعۡتَذِرُواْ لَن نُّؤۡمِنَ لَكُمۡ قَدۡ نَبَّأَنَا ٱللَّهُ مِنۡ
أَخۡبَارِكُمۡۚ وَسَيَرَى ٱللَّهُ عَمَلَكُمۡ وَرَسُولُهُۥ ثُمَّ تُرَدُّونَ إِلَىٰ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَيُنَبِّئُكُم
بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٩٤﴾ سَيَحۡلِفُونَ بِٱللَّهِ لَكُمۡ إِذَا ٱنقَلَبۡتُمۡ إِلَيۡهِمۡ لِتُعۡرِضُواْ عَنۡهُمۡۖ فَأَعۡرِضُواْ
عَنۡهُمۡۖ إِنَّهُمۡ رِجۡسٞۖ وَمَأۡوَىٰهُمۡ جَهَنَّمُ جَزَآءَۢ بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ﴿٩٥﴾ يَحۡلِفُونَ لَكُمۡ لِتَرۡضَوۡاْ
عَنۡهُمۡۖ فَإِن تَرۡضَوۡاْ عَنۡهُمۡ فَإِنَّ ٱللَّهَ لَا يَرۡضَىٰ عَنِ ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡفَٰسِقِينَ ﴿٩٦﴾

**94-96.** (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነርሱ በተመለሳችሁ ጊዜ ምክንያቶቻቸውን ያቀርቡላችኋል። አታመካኙ እናንተን ፈጽሞ አናምንም። አላህ ከወሬዎቻችሁ አስቀድሞ ነግሮናልና። አላህና መልዕክተኛው ሥራችሁን ያያሉ። ከዚያ ሩቅንና ቅርብን ሁሉ ዐዋቂ ወደ ሆነው አላህ ትመለሳላችሁ። ወዲያውም ትሠሩት የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል በላቸው። ከዘመቻ ወደ እነርሱ በተመለሳችሁ ጊዜ ጥፋታቸውን ይቅር እንድትልላቸው ለእናንተ በአላህ ይምላሉ። እነርሱን ተውዋቸው። እነርሱ እርኩሶች ናቸውና። ይሠሩትም በነበረው ኃጢአት መኖሪያቸው ገሀነም ነው። ትወዱላቸው ዘንድ ለእናንተ ይምሉላችኋል። እናንተ ብትወዷቸው አላህ አመፀኛ ህዝቦችን አይወድም።

ٱلۡأَعۡرَابُ أَشَدُّ كُفۡرٗا وَنِفَاقٗا وَأَجۡدَرُ أَلَّا يَعۡلَمُواْ حُدُودَ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ عَلَىٰ رَسُولِهِۦۗ
وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ﴿٩٧﴾

**97.** ዘላን አረቦች በክሕደትና በንፍቅና በጣም የበረቱ፤ አላህ በመልዕክተኛው ላይ ያወረደውን ህግጋት ባለማወቅ የተገቡ ናቸው። አላህ ዐዋቂ፤ ጥበበኛ ነው።

وَمِنَ ٱلۡأَعۡرَابِ مَن يَتَّخِذُ مَا يُنفِقُ مَغۡرَمٗا وَيَتَرَبَّصُ بِكُمُ ٱلدَّوَآئِرَۚ
عَلَيۡهِمۡ دَآئِرَةُ ٱلسَّوۡءِۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ﴿٩٨﴾

**98.** ከዘላኖች መካከል በአላህ መንገድ የሚያወጣውን ገንዘብ እዳ አድርጎ የሚይዝና በእናንተ ላይ የጊዜን መገለባበጥ የሚጠባበቅ ሰው አለ። በእነርሱ ላይ ጥፋቱ ይዞርባቸው። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነው።

وَمِنَ ٱلْأَعْرَابِ مَن يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْـَٔاخِرِ وَيَتَّخِذُ مَا يُنفِقُ قُرُبَٰتٍ عِندَ ٱللَّهِ وَصَلَوَٰتِ ٱلرَّسُولِ ۚ أَلَآ إِنَّهَا قُرْبَةٌ لَّهُمْ ۚ سَيُدْخِلُهُمُ ٱللَّهُ فِى رَحْمَتِهِۦٓ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٩٩﴾

**99.** ከአረብ ዘላኖች መካከል በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምን የሚሰጣቸውንም ምጽዋቶች አላህ ዘንድ መቃረቢያዎችና ወደ መልዕክተኛው ፀሎቶች መዳረሻ አድርጎ የሚይዝ ክፍል አለ። ንቁ፣ እርሷ ለእነርሱ በእርግጥ አቃራቢ ናት። አላህ በችሮታው ውስጥ በገነቱ በእርግጥ ያስገባቸዋል። አላህ መሓሪ፤ አዛኝ ነውና።

وَٱلسَّٰبِقُونَ ٱلْأَوَّلُونَ مِنَ ٱلْمُهَٰجِرِينَ وَٱلْأَنصَارِ وَٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُم بِإِحْسَٰنٍ رَّضِىَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ وَرَضُوا۟ عَنْهُ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى تَحْتَهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًا ۚ ذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴿١٠٠﴾

**100.** ከስደተኞቹም ሆነ ከረዳቶቹ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎችና እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው ሰዎች አላህ የእነርሱን ተግባር ወዶላቸዋል። እና እነርሱም ወደውለታል። በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸውም ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲሆኑ አዘጋጅቶላቸዋል። ይህ ታላቅ እድለኛነት ነው።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከ (97-100) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አቡ አሚር የተባለው መነኩሴ በጃሂሊያ ጊዜ የክርስትናን ሃይማኖት ተቀብሎና በእርሱም ምክንያት ሹመት አግኝቶ ይኖር ነበር። ከዚያም ረሱል ሙሐመድ (ﷺ) ዳዕዋ ሲጀምሩ በጣም ተናደደ። «ስልጣኔን አጣ ይሆናል» በሚል ስጋትም ተወጠረና ነብዩን (ﷺ) ማጥላላትና ማውገዙን ተያያዘው። ይባስ ብሎ ነብዩን (ﷺ) «አንተን የሚዋጋ ባገኘሁ ቁጥር አብሬ እዋጋለሁ» በማለት አቋሙንና ለኢስላም ያለውን ጥላቻ ይፋ አድርጎ በጠላትነት መንቀሣቀስ ጀመረ። ከዚያም ነብዩ (ﷺ) አቡ አሚር አልፋሲቅ ሲሉ ሰየሙት። በሁነይን ዘመቻ ዕለት ከሐዋዚን ሰዎች ጐን ተሰልፎ ሙስሊሞችን ሊዋጋ ቢቆምም ሙስሊሞች የሁነይንን ዘመቻ በድል በማጠናቀቃቸው ወደሻም ተሰደደና ለአስመሳዮች መስጊድ እንዲሰሩለትና ነብዩና (ﷺ) ተከታዮቻቸውን በዚህ መስጊድ እንዲሰግዱ ጥሪ እንዲያደርጉላቸው እነርሱም ጥሪውን አክብረው ሲመጡ ባልተዘጋጁበት ሁኔታ የሙስሊሙን ሀይል የሚያጠቃ ሰራዊት እንዲያዘጋጁ ተንኮል ሸርበ። አስመሳዮችም የሴራው ተካፋይ በመሆን በቁባ መስጊድ አጠገብ ሌላን መስጊድ ሠሩና ለረሱል ሙሐመድ (ﷺ) ለደካሞች የሚሆን መስጊድ ሠርተናልና መጥተው ይጐብኙልን በውስጧም ይስገዱ ሲሉ ጠየቋቸው። ነብዩም (ﷺ) የነዚህን አስመሣዮች ተንኮል ባለመረዳት ልብሳቸውን አምጡልኝ ብለው ለባብሰው ለመሄድ ሲዘገጃጁ አላህ በዚህ መስጊድ እንዳይሰግዱና ለተንኮል ስራ የተዘጋጀ መስጊድ መሆኑን በማጋለጥ ከ (105-110) ያሉትን አናቅፅ አወረደ። ነብዩም (ﷺ) ሱሀቦችን ጠርተው ይህን ለተንኮል የተሰራ መስጊድ (መስጂድ አል ዲራር) እንዲያፈራርሱ አዘዟቸው። መስጊዱንም አስፈረሱትና ፍርስራሹም እንዲቃጠል አደረጉ። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَمِمَّنْ حَوْلَكُم مِّنَ ٱلْأَعْرَابِ مُنَٰفِقُونَ ۖ وَمِنْ أَهْلِ ٱلْمَدِينَةِ مَرَدُوا۟ عَلَى ٱلنِّفَاقِ لَا تَعْلَمُهُمْ ۖ
نَحْنُ نَعْلَمُهُمْ ۚ سَنُعَذِّبُهُم مَّرَّتَيْنِ ثُمَّ يُرَدُّونَ إِلَىٰ عَذَابٍ عَظِيمٍ ﴿١٠١﴾ وَءَاخَرُونَ ٱعْتَرَفُوا۟ بِذُنُوبِهِمْ
خَلَطُوا۟ عَمَلًا صَٰلِحًا وَءَاخَرَ سَيِّئًا عَسَى ٱللَّهُ أَن يَتُوبَ عَلَيْهِمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٠٢﴾

**101-102.** በዙሪያችሁም ካሉት ከዐረብ ዘላኖች መናፍቃን አሉ። ከመዲና ሰዎችም በንፍቅና ላይ በማመፅ የዘወተሩ አሉ። አታውቃቸውም። እኛ እናውቃቸዋለን። ሁለት ጊዜ እንቀጣቸዋለን። ከዚያም ወደ ታላቅ ቅጣት ይመለሳሉ። ሌሎችም ኃጢአቶቻቸውን የተናዘዙ መልካም ሥራንና ሌላን መጥፎ ሥራ የቀላቀሉ አሉ። አላህ ከነሱ ፀፀታቸውን ሊቀበል ይከጀላል። አላህ መሓሪ፣ አዛኝ✷ ነውና።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ዛሬ ሌሊት ሁለት ጎብኚዎች በሕልሜ ወደኔ መጡና ከወርቅና ከብር ጡቦች ወደ ተገነባች ከተማ ይዘውኝ ሄዱ። በዚያ ከተማ ውስጥ ከፊል የፊት ገፅታቸው ከዚህ በፊት አይታችሁት የማታውቁት ውብ የሆነ ሌላኛው ከፊል ገፅታቸው ደግሞ ከዚህ በፊት አይታችሁት የማታውቁት አስቀያሚ የሆኑ ሰዎች ይገኛሉ። እነዚህ ሁለት ጎብኚዎች ለነዚህ አይነቶቹ ሰዎች «ሂዱና ራሳችሁን እዚያ ወንዝ ውስጥ ንከሩት» አሏቸው። ሰዎቹም ራሳቸውን ወንዙ ውስጥ ነከሩና ተመልሰው ወደኛ መጡ። በዚህ ጊዜ ከዚህ በፊት በከፊል ገፅታቸው ላይ የነበረው አስቀያሚ ገፅታ ጠፍቶ በጣም ውብ በሆነ ገፅታ ተለውጦ ነበር። ጎብኚዎቹም «ይህ ዝቅተኛው የጀነት ክፍል ነው ያ ደግሞ ያንተ ቦታ ነው። እነዚያ ከፊል ገፅታቸው ውብና አስቀያሚ የሆኑ ሰዎች እነዚያ መልካም ከሆኑት ስራዎቻቸው ጋር መጥፎ ስራዎችን የሚደባልቁ ሰዎች ናቸው። ዳሩ ግን አላህ ይቅር ብሏቸዋል» አሉ።

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (93-102) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. እውነተኛ ምክንያት ያለው ሆኖ ከጂሃድ የቀረን ሙስሊም ማስቸገር እንደማይፈቀድና በቂ ሸሪዓዊ ምክንያት ያለው ሙስሊም ጉዳዩን አስረድቶና ምክንያቱን አቅርቦ ፈቃድ በመጠየቁ ወንጀል እንደሌለበት፣
2. አስመሳዮች ልክ እንደ ከሓዲያን ልባቸው የቆሸሸ መንፈሳዊ ጎናቸው የተበከለ መሆናቸውን፣
3. የገጠር ነዋሪ የሆኑ ዘላን ሕዝቦች ብዙውን ጊዜ ትምህርቶችን የሚያገኙበት አጋጣሚና እድል የሌላቸው በመሆኑ ኢስላማዊ እውቀቶችንም ሳያገኙ እንደሚያመልጧቸው፣
4. ለአላህ ተብሎ የሚለገሱ ገንዘቦች ተደራራቢ ምንዳ የሚያስጡ ስለመሆኑ፣
5. የገጠር ነዋሪ የሆኑ ዘላን ህዝቦች እንደከተሜው ሁሉ ደግም መጥፎም እንዳላቸው፣
6. ኩፍርና ኒፋቅ እንደሁኔታው እንደሚጨምርና እንደሚቀንስ፣
7. ስለ እውቀት አስፈላጊነትና ክብር፣ እውቀት የሌለው ሰው ለከፉ ነገር በቀላሉ እንደሚጋለጥ፣
8. ከትምህርቱ ሁሉ ዋናው የአላህን ህግጋት የሚያሳውቁ ትምህርቶች መሆናቸውን፣
9. ሙዕሚን የሆነ ሰው ያለበትን ኃላፊነት ሲወጣ በደስተኝነት መሆን እንዳለበት፣
10. ለመልካም መሽቀዳደም የሚያስገኘው ምንዳ በዚያው ልክ የበዛ ስለ መሆኑ፣
11. የነብዩ (ﷺ) ጓደኞች በእሳት ተፈትነው የወጡ የኢስላም የቁርጥ ቀን ልጆች በመሆናቸው ከሌላው ትውልድ ብልጫ የሚሰጣቸው የምርጥ ትውልድ ስብስብ መሆናቸውንና የእነርሱን ፈለግ የተከለተሉት ተከታዮቻቸውም ከፍ ያለ ክብርና ማዕረግ የሚሰጣቸው መሆኑን፣

12. በሰዎች ልብ ውስጥ ያለውን ሀሳብና በልቦቻቸው ውስጥ የሚመላለሰውን ድብቅ ፍላጎታቸውን ከአላህ ሌላ ማንም የማያውቅ ስለ መሆኑ፤
13. ተውሒድ ያላቸው ሆነው አንዳንድ ስህተቶችን የሰሩ ሙስሊሞች የአላህን ምህረት ለማግኘት ዘወትር መጣር እንጂ ከርሱ ምህረት ተስፋ መቁረጥ እንደሌለባቸው፤
14. በሁሉም የገንዘብ አይነቶች ዘካ ግዴታ እንደሆነ፤
15. ማንም ሙስሊም ራሱን ሊያፀዳ የሚችለው የገንዘብ ዘካውን ሲከፍል እንደሆነ፤
16. ዘካውን ለከፈለ ሰው ተቀባዩ መሪ ወይም ተወካዩ በግልፅ ዱአ ማድረግ እንዳለበት፤
17. ሙስሊሞችን በጥሩ አንደበት ማስደሰት እንዳለብን፤
18. ኸይርን ለሰራ ሁሉ ማበረታታትና ለሱ ዱአ ማድረግ እንዳለብን፤

خُذۡ مِنۡ أَمۡوَٰلِهِمۡ صَدَقَةٗ تُطَهِّرُهُمۡ وَتُزَكِّيهِم بِهَا وَصَلِّ عَلَيۡهِمۡۖ
إِنَّ صَلَوٰتَكَ سَكَنٞ لَّهُمۡۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ١٠٣

**103.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከገንዘቦቻቸው የምታጠራቸውና የምታፋፋቸውን ምጽዋት ያዝ። ለእነርሱም ፀልይላቸው። ፀሎትህ ለእነርሱ እርጋታ ነውና። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነው።

أَلَمۡ يَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ هُوَ يَقۡبَلُ ٱلتَّوۡبَةَ عَنۡ عِبَادِهِۦ وَيَأۡخُذُ ٱلصَّدَقَٰتِ
وَأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ١٠٤

**104.** አላህ እርሱ ከባሮቹ ንሰሃን የሚቀበልና ምጽዋቶችን የሚወስድ፣ አላህ ብቸኛ ፀፀትን ተቀባይና አዛኝ መሆኑን አያውቁምን?

وَقُلِ ٱعۡمَلُواْ فَسَيَرَى ٱللَّهُ عَمَلَكُمۡ وَرَسُولُهُۥ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَۖ وَسَتُرَدُّونَ إِلَىٰ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِ
وَٱلشَّهَٰدَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ١٠٥ وَءَاخَرُونَ مُرۡجَوۡنَ لِأَمۡرِ ٱللَّهِ إِمَّا يُعَذِّبُهُمۡ
وَإِمَّا يَتُوبُ عَلَيۡهِمۡۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ١٠٦

**105-106.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሰዎች ሆይ)፣ ሥሩ። አላህ መልዕክተኛውና ምዕመናንም ሥራችሁን በእርግጥ ያያሉና በላቸው። ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ወደ ሆነው አላህ በእርግጥ ትመለሳላችሁ። ትሰሩት የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል (በላቸው)። ሌሎችም የአላህን ውሳኔ ትዕዛዝ እንዲጠብቁ የተቆዩ ህዝቦች አሉ። ይቀጣቸዋል ወይም ፀፀታቸውን ይቀበላቸዋል። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነውና።

وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مَسۡجِدٗا ضِرَارٗا وَكُفۡرٗا وَتَفۡرِيقَۢا بَيۡنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَإِرۡصَادٗا لِّمَنۡ حَارَبَ ٱللَّهَ
وَرَسُولَهُۥ مِن قَبۡلُۚ وَلَيَحۡلِفُنَّ إِنۡ أَرَدۡنَآ إِلَّا ٱلۡحُسۡنَىٰۖ وَٱللَّهُ يَشۡهَدُ إِنَّهُمۡ لَكَٰذِبُونَ ١٠٧ لَا تَقُمۡ
فِيهِ أَبَدٗاۚ لَّمَسۡجِدٌ أُسِّسَ عَلَى ٱلتَّقۡوَىٰ مِنۡ أَوَّلِ يَوۡمٍ أَحَقُّ أَن تَقُومَ فِيهِۚ فِيهِ رِجَالٞ يُحِبُّونَ
أَن يَتَطَهَّرُواْۚ وَٱللَّهُ يُحِبُّ ٱلۡمُطَّهِّرِينَ ١٠٨ أَفَمَنۡ أَسَّسَ بُنۡيَٰنَهُۥ عَلَىٰ تَقۡوَىٰ مِنَ ٱللَّهِ وَرِضۡوَٰنٍ
خَيۡرٌ أَم مَّنۡ أَسَّسَ بُنۡيَٰنَهُۥ عَلَىٰ شَفَا جُرُفٍ هَارٖ فَٱنۡهَارَ بِهِۦ فِي نَارِ جَهَنَّمَۗ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي
ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٠٩ لَا يَزَالُ بُنۡيَٰنُهُمُ ٱلَّذِي بَنَوۡاْ رِيبَةٗ فِي قُلُوبِهِمۡ إِلَّآ أَن تَقَطَّعَ قُلُوبُهُمۡۗ
وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ١١٠

**107-110.** እነዚያ (ምዕመናንን) ለመጉዳት ክህደትንም ለማበረታታት ከምዕመናንም መካከል ለመለያየት ከአሁን በፊት አላህንና መልዕክተኛውን የተዋጋውን ሰው ለመጠባበቅ መስጊዱን የሠሩት ሰዎች (ከእነርሱ ናቸው)። መልካምን ሥራ እንጂ ሌላ አልሻንም ሲሉ በእርግጥ ይምላሉ። አላህ ደግሞ ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል። በእርሱ ውስጥ በፍፁም አትስገድ። ይልቁንም ከመጀመሪያ ቀን ይዞ በአላህ ፍራቻ ላይ የተመሠረተው (የቁባ) መስጊድ በውስጡ ልትሰግድበት የተገባው ነው። በእሱ ውስጥ መጥራራትን የሚወዱ ወንዶች አሉ። አላህ ተጥራሪዎችን ይወዳል። አላህን በመፍራትና ውዴታውን በመፈለግ ላይ ግንቡን የመሠረተ ሰው ይበልጣልን? ወይስ ጎርፍ በሸረሸረው ለመናድ በተቃረበ ገደል አፋፍ ላይ ግንቡን የመሠረተውና በእርሱ ይዞት በገሀነም እሳት ውስጥ የወደቀ (ይበልጣል?) አላህ በደለኞች ሕዝቦችን አይመራም። ያ፣ የካቡት ግንባቸው ልቦቻቸው በሞት ካልተቆራረጡ በቀር በልቦቻቸው ውስጥ የመጠራጠር ምክንያት ከመሆን አይወገድም። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነው።

ከንሰሓ መግባት ምዕራፍ (107) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በኒ አምሮች የቁባን መስጂድ ሠርተው ወደ ነብዩ (ﷺ) «ሠላት ይስገዱልን» ብለው ላኩባቸውና ሄደው ሠገዱላቸው። በኋላ የበኒ አምሮች ወንድሞች ቅናት አደረባቸውና እኛም መስጂድ እንስራና ነብዩ (ﷺ) መጥተው እንዲሠግዱልን እንላክባቸው ተባባሉ። አቡ አሚር የተባለው ሠውዬም ከሻም ሲመጣ እሱም ይስገድበት። በማለታቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

۞ إِنَّ ٱللَّهَ ٱشۡتَرَىٰ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ أَنفُسَهُمۡ وَأَمۡوَٰلَهُم بِأَنَّ لَهُمُ ٱلۡجَنَّةَۚ يُقَٰتِلُونَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ
فَيَقۡتُلُونَ وَيُقۡتَلُونَۖ وَعۡدًا عَلَيۡهِ حَقّٗا فِي ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَٱلۡإِنجِيلِ وَٱلۡقُرۡءَانِۚ وَمَنۡ أَوۡفَىٰ بِعَهۡدِهِۦ

مِنَ ٱللَّهِۚ فَٱسۡتَبۡشِرُواْ بِبَيۡعِكُمُ ٱلَّذِي بَايَعۡتُم بِهِۦۚ وَذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ١١١ ٱلتَّٰٓئِبُونَ
ٱلۡعَٰبِدُونَ ٱلۡحَٰمِدُونَ ٱلسَّٰٓئِحُونَ ٱلرَّٰكِعُونَ ٱلسَّٰجِدُونَ ٱلۡأٓمِرُونَ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَٱلنَّاهُونَ
عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَٱلۡحَٰفِظُونَ لِحُدُودِ ٱللَّهِۗ وَبَشِّرِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١١٢

**111-112.** አላህ ከአማኞች ነፍሶቻቸውንና ገንዘቦቻቸውን ገነትን ለእነርሱ ብቻ በማድረግ ገዛቸው። በአላህ መንገድ ላይ ይጋደላሉ። እናም ይገድላሉ። ይገደላሉም። በተውራት በኢንጂልና በቁርኣንም የተነገረውን ተስፋ በእርሱ ላይ አረጋገጠ። ከአላህ የበለጠ በቃል ኪዳኑ የሚሞላ ማን ነው? በዚያም በእርሱ በተሻሻጣችሁበት ሽያጫችሁ ተደሰቱ። ይህ ታላቅ ዕድል ነው።*1 ነእነርሱ ተፀፃቾች፤ ተገዢዎች፣ አመስጋኞች፣ ፆመኞች፣ (በሶላት) አጎንባሾች፣ በግንባር ተደፊዎች፣ በበጎ ሥራ አዛዦች፣ ከክፉ ከልካዮች እና የአላህን ሕግጋት ጠባቂዎች ናቸው። አማኞችንም አብስር።*2

*1 (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ለአንድ በሱ መንገድ ላይ ለተጋደለ፤ ተጋድሎውን ሲያደርግ በአላህ መንገድ ላይ መዋጋትንና የቃሉን ትክክለኛነት አምኖ ለተዋጋ ሰው ጀነትን እንደሚያስገባው ወይም ወደነበረበት መኖሪያው ምንዳውንና ሀብቱን ሊመልሰው ዋስትና ሰጥቷል።

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ጃቢር ብኑ ዐብደላህ እንዳስተላለፉት በኡሑድ ጦርነት ጊዜ አንድ ሰው ወደ ነብዩ መጣና «መስዋዕትነትን ካገኘሁ የት እንደምሆን ሊነግሩኝ ይችላሉን?» ሲል ጠየቃቸው። እሳቸውም «ጀነት ውስጥ ነዋ» ሲሉ መለሱለት። በእጁ ይዟቸው የነበሩትን የቴምር ፍሬዎች ወረወረና መስዋእት እስኪሆን ድረስ ተጋደለ።

(ሐ) የአላህ መልዕክተኛ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «በዒናህ ከተገበያያችሁ፤ የከብቶችን ጭራ ከተከተላችሁና በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግን ትግል ከተዋችሁ አላህ ወደ ሃይማኖታችሁ እስከትመለሱ ድረስ ውርደትን በላያችሁ ላይ ያንሰራፋባችኋል።»

«በዒናህ መገበያየት» ማለት አንድ ሰው አንድን ዕቃ ለሌላ ሰው በተወሰነ ዋጋ ከሸጠ በኋላ ይህንኑ እቃ ከገዢው ላይ በጣም ዝቅ ባለ ዋጋ መግዛት ማለት ነው።

*2 ሰህል ብኑ ሰዕድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በሁለቱ መንገጭላ መካከልና በሁለት እግሮቹ መካከል ላሉት ነገሮች ዋስትና ለሰጠኝ ማንኛውም ሰው እኔ ጀነትን ዋስትና እሰጠዋለሁ።»

እዚህ ላይ በሁለቱም መንገጭላዎች መካከል ያለው ነገር ምላስ ሲሆን የሐዲሱ ፅንሰ ሃሳብ በምላሱ ክፉ ነገር ላለመናገርና ሰዎችን ላለማማት ዋስትና የሰጠ ሰው ማለት ነው። በሁለት እግሮቹ መካከል የሚገኘው ብልት በኢስላም ያልተፈቀደ ወይም ክልክል የሆነ ግብረ ስጋ ግንኙነት ላይፈፅምበት ዋስትና የሰጠ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ያመለክታል።

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከ (103-112) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. (ምፅዋት) በኢስላም ወንጀሎችን የሚያሰርዝ መልካም ተግባር ስለመሆኑ፤
2. የሰው ልጅ ምንጊዜም የህይወት ጉዞው የአላህን ቅጣት በመፍራትና ምህረቱንና ጀነቱን ተስፋ በማድረግ መሀከል ሚዛናዊ ሆኖ መቀጠል እንዳለበት፤

3. አስመሳዮች (አስመሳዮች) ኢስላምን ለማዳከም በመወጠን ከፍተኛ ሴራ ሸርበው እንደነበር የሚያስተምር (ሚያጋልጥ) ቁርአናዊ አንቀፅ፤
4. ለክብርና ለዝና የሚደረጉ እሽቅድድሞች ክርክሮች ለችግሮች ሁሉ መንስኤ እንደሆኑ፤
5. መናፍቃን (አስመሳዮች) በሚያስወሩት የውሸት ፕሮፖጋንዳ መረታትና መሞኘት ግለሰባዊና ማህበራዊ የእምነት ደረጃን የሚያበላሽ በመሆኑ ለአስመሳዮች (ለአስመሳዮች) ወሬ ስራ መፈታት የማይገባ ስለ መሆኑ፤
6. ሙስሊሞችን ለመከፋፈል ኃይላቸውን ለማዳከም ታስቦ የሚገነባ መስጊድ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ በጣም የሚያመዝን በመሆኑ መፍረሱ አማራጭ የሌለው መፍትሄ መሆኑን፤
7. እንደ አስፈላጊነቱ የአካልም ሆነ የመንፈስ ንፅህናን መጠበቅ ኢስላማዊ ግዴታ መሆኑን፤
8. ስለ ቁባ መስጊድ ክብርና ትልቅነት፤
9. ሌላን መስጊድ ለመጉዳት ወይም ለማዳከም ታስበው የሚሰሩ መስጊዶች ላይ ሶላት መስገድም ሆነ በግንባታው ላይ መሳተፍ ክልክል መሆኑን፤
10. አንድ ስራ በራሱ መልካም ነገር ቢሆንም በተግባሪው ንያ ወደ መጥፎነት እንደሚቀየር፤
11. የሙስሊሞችን አንድነት ሊከፋፍል የሚችልን ነገር ሁሉ መፈፀም ክልክል መሆኑን፤
12. በወንጀል መፈፀሚያ ቦታዎች ውስጥ ሶላት መስገድ ክልክል መሆኑን፤
13. ወንጀል በሰዎች ላይ ተፅዕኖ እንደሚያሳድር ሁሉ በቦታም ላይ ተፅዕኖ እንደሚሳድር፤
14. አላህን የሚያስቆጣም ወይም አንድን ሙስሊም የሚጎዳ ተግባር ሁሉ የተከለከለ መሆኑን፤
15. ስለ ነብዩ (ﷺ) መስጊድ (የመዲና መስጊድ) ክብር፤
16. አላህ ለባሪያዎቹ የዋለውን ፀጋ ለርሱ አላማ ያውሉ ዘንድ ፈቃደኛ ከሆኑ በእርሱ በኩል በድጋሚ ለዚህ ፈቃደኝነታቸው ተገቢውን መልካም አፀፋ ለመስጠት ቃል መግባቱን፤
17. ጂሃድ ላይ በሕይወትና በንብረት መስዕዋት ለመሆን መዘጋጀት ያለውን ከፍ ያለ ምንዳ፤
18. አማኝ የሆነ ሰው ነፍሱም ሆነ ቁሳዊ ንብረቱ በሙሉ የአላህ መሆኑን ማወቅ እንደሚገባውና ነፍሱና ገንዘቡ የአላህ ነው በሚል ስሜት ተገፋፍቶ በራሱም ሆነ በንብረቱ ላይ አደጋ ማድረስ እንደማይችል፤
19. የትክክለኛ አማኝነት መገለጫ የሆኑት ባህሪያት ዝርዝር ይዘቶች የሚያሳይ ቁርአናዊ አንቀፅ የሚሉት ናቸው፡

مَا كَانَ لِلنَّبِيِّ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَن يَسۡتَغۡفِرُواْ لِلۡمُشۡرِكِينَ وَلَوۡ كَانُوٓاْ أُوْلِي قُرۡبَىٰ مِنۢ بَعۡدِ مَا
تَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُمۡ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَحِيمِ ﴿١١٣﴾ وَمَا كَانَ ٱسۡتِغۡفَارُ إِبۡرَٰهِيمَ لِأَبِيهِ إِلَّا عَن مَّوۡعِدَةٖ
وَعَدَهَآ إِيَّاهُ فَلَمَّا تَبَيَّنَ لَهُۥٓ أَنَّهُۥ عَدُوّٞ لِّلَّهِ تَبَرَّأَ مِنۡهُۚ إِنَّ إِبۡرَٰهِيمَ لَأَوَّٰهٌ حَلِيمٞ ﴿١١٤﴾ وَمَا كَانَ
ٱللَّهُ لِيُضِلَّ قَوۡمَۢا بَعۡدَ إِذۡ هَدَىٰهُمۡ حَتَّىٰ يُبَيِّنَ لَهُم مَّا يَتَّقُونَۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ ﴿١١٥﴾

**113-115.** ለመልክተኛውም ሆነ ለእነዚያ በእሱ ላመኑት ሰዎች ለአጋሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች ቢሆኑም እንኳ ከሓዲያን የእሳት ጓዶች መሆናቸው ከተገለፀላቸው በኋላ የአላህን ምሕረት ሊለምኑላቸው የሚገባ አይደለም፡፡ ኢብራሂም ለአባቱ ምህረትን መለመን ቀድሞ ገብቶለት የነበረውን ቃል

ለመሙላት እንጂ ለሌላ አልነበረም። እናም እርሱም የአላህ ጠላት መሆኑ በተገለፀለት ጊዜ ከእርሱ ራቀ ተወው። ኢብራሂም በእርግጥ ሩህሩህና ታጋሽ ነበርና። አላህ ህዝቦችን ካቀናቸው በኋላ የሚጠነቀቁትን ነገር እሥከሚገልጽላቸው ድረስ ሳያውቁ በሰሩት ጥፋት ጥፋተኛ የሚያደርግ ጌታ አይደለም። አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነውና።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ (115) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ለሞቱ ጣኦት አምላኪያን የቤተሰብ አባላት ከአላህ ምህረት የለመኑ ሙስሊሞች ክልክል መሆኑን ሲሰሙ በጣም ተደናግጠው ስለነበር «ሳታውቁት በሰራችሁት ምንም የለባችሁም» የሚለው ይህ አንቀፅ የወረደው።

إِنَّ ٱللَّهَ لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۚ
وَمَا لَكُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ مِن وَلِيّٖ وَلَا نَصِيرٖ ﴿١١٦﴾

**116.** አላህ የሰማያትና የምድር ንግስና የእርሱ ብቻ ነው። ህያው ያደርጋል። ይገድላልም። ለእናንተም ከእርሱ በቀር ጠባቂም ሆነ ወዳጅ የላችሁም።

لَّقَد تَّابَ ٱللَّهُ عَلَى ٱلنَّبِيِّ وَٱلۡمُهَٰجِرِينَ وَٱلۡأَنصَارِ ٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُ فِي سَاعَةِ ٱلۡعُسۡرَةِ مِنۢ بَعۡدِ
مَا كَادَ يَزِيغُ قُلُوبُ فَرِيقٖ مِّنۡهُمۡ ثُمَّ تَابَ عَلَيۡهِمۡۚ إِنَّهُۥ بِهِمۡ رَءُوفٞ رَّحِيمٞ ﴿١١٧﴾

**117.** በመልክተኛው በእነዚያም በችግሩ ጊዜ (በተቡክ ዘመቻ) ከእነርሱ የከፊሎቹ ልቦች ለመቅረት ሊዘነበሉ ከተቃረቡ በኋላ በተከተሉት ስደተኞችና ረዳቶች ላይ አላህ በእርግጥ ፀፀታቸውን ተቀበለ። ከዚያ ከእነርሱ ንሰሃ መግባታቸውን ተቀበለ። እርሱ (አላህ) ለእነርሱ ሩህሩህና አዛኝ ነውና።

وَعَلَى ٱلثَّلَٰثَةِ ٱلَّذِينَ خُلِّفُواْ حَتَّىٰٓ إِذَا ضَاقَتۡ عَلَيۡهِمُ ٱلۡأَرۡضُ بِمَا رَحُبَتۡ
وَضَاقَتۡ عَلَيۡهِمۡ أَنفُسُهُمۡ وَظَنُّوٓاْ أَن لَّا مَلۡجَأَ مِنَ ٱللَّهِ إِلَّآ إِلَيۡهِ ثُمَّ تَابَ عَلَيۡهِمۡ لِيَتُوبُوٓاْۚ
إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلتَّوَّابُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١١٨﴾

**118.** በእነዚያም ወደ ኋላ በቀሩት በሶስቱ ሰዎች ላይ ምድር ከስፋቷ ጋር በእነርሱ ላይ እስከምትጠብባቸው ነፍሶቻቸውም በእነርሱ ላይ እስከምትጠብባቸው ከአላህም ወደ እርሱ ብቻ እንጂ ሌላ መጠጊያ አለመኖሩን እስከሚያረጋግጡ ድረስ በተቆዩት ላይ አላህ ፀፀትን ተቀበለ። ከዚያ ይፀፀቱ ዘንድ ወደ ፀፀት መራቸው። አላህ ፀፀትን ተቀባይና አዛኝ ነውና።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَكُونُواْ مَعَ ٱلصَّـٰدِقِينَ ﴿١١٩﴾ مَا كَانَ لِأَهْلِ ٱلْمَدِينَةِ وَمَنْ
حَوْلَهُم مِّنَ ٱلْأَعْرَابِ أَن يَتَخَلَّفُواْ عَن رَّسُولِ ٱللَّهِ وَلَا يَرْغَبُواْ بِأَنفُسِهِمْ عَن نَّفْسِهِۦ ۚ ذَٰلِكَ
بِأَنَّهُمْ لَا يُصِيبُهُمْ ظَمَأٌ وَلَا نَصَبٌ وَلَا مَخْمَصَةٌ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَلَا يَطَـُٔونَ مَوْطِئًا يَغِيظُ
ٱلْكُفَّارَ وَلَا يَنَالُونَ مِنْ عَدُوٍّ نَّيْلًا إِلَّا كُتِبَ لَهُم بِهِۦ عَمَلٌ صَـٰلِحٌ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجْرَ
ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٢٠﴾ وَلَا يُنفِقُونَ نَفَقَةً صَغِيرَةً وَلَا كَبِيرَةً وَلَا يَقْطَعُونَ وَادِيًا إِلَّا كُتِبَ لَهُمْ
لِيَجْزِيَهُمُ ٱللَّهُ أَحْسَنَ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿١٢١﴾ ۞ وَمَا كَانَ ٱلْمُؤْمِنُونَ لِيَنفِرُواْ كَآفَّةً ۚ فَلَوْلَا
نَفَرَ مِن كُلِّ فِرْقَةٍ مِّنْهُمْ طَآئِفَةٌ لِّيَتَفَقَّهُواْ فِى ٱلدِّينِ وَلِيُنذِرُواْ قَوْمَهُمْ إِذَا رَجَعُوٓاْ إِلَيْهِمْ
لَعَلَّهُمْ يَحْذَرُونَ ﴿١٢٢﴾ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ قَـٰتِلُواْ ٱلَّذِينَ يَلُونَكُم مِّنَ ٱلْكُفَّارِ وَلْيَجِدُواْ
فِيكُمْ غِلْظَةً ۚ وَٱعْلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلْمُتَّقِينَ ﴿١٢٣﴾

**119-123.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህን በትክክል ፍሩ። ከእውነተኞችም*1 ጋር ሁኑ። የመዲና ሰዎችና በዙሪያቸው ያሉት የዘላን ዓረብ ህዝቦች ከአላህ መልዕክተኛ ጥሪ ወደ ኋላ ሊቀሩና ነፍሶቻቸውንም ከነፍሱ አብልጠው ሊወዱ አይገባቸውም ነበር። ይህም የሆነው ለእነርሱ መልካም ሥራ የሚጻፍላቸው ቢሆን እንጂ በአላህ መንገድ ላይ ጥምም ድካምም ርሀብም የማይነካቸው ከሓዲያንንም የሚያስቆጭን ስፍራ የማይረግጡ ከጠላትም የሚጎዳን ነገር የማያገኙ በመሆናቸው ነው። አላህ የመልካም ሠሪዎችን ምንዳ*2 አያጠፋምና። ትንሽንም ትልቅንም ልግስና አይለግሱም ወንዝንም አያቋርጡም አላህ ይሠሩት ከነበረው የበለጠን ምንዳ ይመነዳቸው ዘንድ ለእነርሱ የሚጻፍላቸው ቢሆን እንጂ። ምዕመናንም (ከነብዩ ጋር ካልሆነ) በሙሉ ወደ ዘመቻ ሊወጡ አይገባም። ከእነርሱ ውስጥ ከየክፍሉ አንዲት ጭፍራ ለምን አትወጣም ሌሎች ሃይማኖትን እንዲማሩና ወገኖቻቸው ወደ እነርሱ በተመለሱ ጊዜ እንዲጠነቀቁ ይገስጿቸው ዘንድ (ለምን አይማሩም?)።*3 እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ እነዚያን በአቅራቢያችሁ ያሉትን ከሓዲያን ተዋጉ። ከናንተም ብርታትን ያግኙ።*4 አላህም ከሚጠነቀቁት ጋር መሆኑን እወቁ።

*1 በኢስላም መመመሪያ በሁሉም ነገር ከእውነተኞች ጋር መሆን አማራጭ የሌለው ወሳኝ ነው። እውነተኝነትን የሚያደንቁ ብሎም ወደ እሱ የሚገፋፉ የቁርአንና የሐዲስ መረጃዎች ብዙ ናቸው። ሰለፎችም ስለዚሁ ብዙ ብለዋል። በዘመናችን የነገሰው ዉሼት በቀደምት ሙስሊሞች ዘንድ ምን ያህል የረከሰ እንደነበር ጥቂቶችን እንመልከት።

(ሀ) ከቁርአን:-

1. በኣሊ ዒምራን **(17)** ኛው፤
2. በአልማኢደህ **(119)** ኛው አንቀፅ፤
3. በአል አህዛብ **(35)** ኛው፤
4. ዩሱፍ **(51)** ኛው ያሉትን እንድትመለከቱና እወነት የቱን ያህል ትልቅ ነገር እንደሆነ ትገነዘባላችሁ።

(ለ) ከሐዲስ:-

1. ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «እውነተኝነት ወደ ትክክለኛ መንገድ ይመራል። ትክክለኛ መንገድም ወደ ጀነት ይመራል። አንድ ሰው እውነተኛ ሰው እስከሚሆን ድረስ እውነትን እየተናገረ ይኖራል። ሀሰተኝነት ወደ መጥፎ ነገር ይመራል። መጥፎ ነገርም ወደ እሳት ይመራል። አንድ ሰው አላህ ዘንድ ሀሰተኛ ተብሎ እስኪፃፍ ድረስ ሀሰትን ይናገራል።
2. ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «የአስመሳዮች ሰው መገለጫዎች ሶስት ናቸው። እነርሱም:- በሚናገርበት ወቅት ይዋሻል። ቃል ኪዳን በገባ ቁጥር ቃልኪዳኑን ያፈርሳል። ምንም አይነት እምነት ቢሰጠው እምነቱን ይክዳል።
3. ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በሕልሜ ሁለት ሰዎች ወደ እኔ መጡ እንዲህም አሉ «ያ ሁለት ጉንጮቹ እስከ ጆሮዎቹ ድረስ የሚቀደዱት ሰው ውሸታም የነበረ ሰው ነው» ይህ ሰው ውሸት ይናገራል። ሰዎቹም የእሱ ውሸት አለም ላይ እስኪሰራጭ ያወራሉ። እሱም የትንሳኤ ቀን እስኪከሰት ድረስ እንዲህ ተደርጎ ይቀጣል።

✶2 (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በቅንነት ኢስላምን ለተቀበለ ሰው አላህ የቀድሞዎቹን ወንጀሎቹን በሙሉ ይምርለታል። ከዚያ በኋላ ምንዳዎች መመዝገብ ይጀምራሉ። የሰራቸው መልካም ስራዎች ምንዳ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ ሲፃፍ የሰራው መጥፎ ተግባር ምንዳ ግን አላህ እስኪምርለት ድረስ እንዳለ ይቀራል።»

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «ከመካከላችሁ አንዱ ሃይማኖቱን በደንብ ከተከተለ የሰራቸው መልካም ስራዎች ምንዳ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፎ ሆነው ይፃፉለታል። የሰራቸው መጥፎ ስራዎች ምንዳ ግን እንዳለ ሆኖ ይፃፍበታል»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በቅንነት ኢስላምን ለተቀበለ ሰው አላህ የቀድሞዎቹን ወንጀሎቹን በሙሉ ይምርለታል። ከዚያ በኋላ ምንዳዎች መመዘግብ ይጀምራሉ። የሰራቸው መልካም ስራዎች ምንዳ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፍ ሲፃፍ የሰራው መጥፎ ተግባር ምንዳ ግን አላህ እስኪምርለት ድረስ እንዳለ ይቀራል።»

(ሐ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «ከመካከላችሁ አንዱ ሃይማኖቱን በደንብ ከተከተለ የሰራቸው መልካም ስራዎች ምንዳ ከአስር እስከ ሰባት መቶ እጥፎ ሆነው ይፃፉለታል። የሰራቸው መጥፎ ስራዎች ምንዳ ግን እንዳለ ሆኖ ይፃፍበታል»

✶3 ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «አላህ መልካምን ነገር ለሻለት ሰው የሃይማኖት እውቀትና ግንዛቤ ይሰጠዋል።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በሁለት ነገሮች እንጂ ቅናት የለም። አንደኛው አላ ገንዘብ ሰጥቶት በአግባቡ ወጪ ያደረገው ሲሆን ሁለተኛው አላህ ትበኢብኑ ሰጥቶት በርሱ መሰረት የሚፈርድና እርሱንም የሚያስተምር ነው።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ እኔን የላከበት ቅን መመሪያና እውቀት ልክ ከመሬት ላይ እንዳፈረ ዝናብ ማለት ነው። ከፊሉ የመሬት ክፍል ጥሩ ይሆንና ዝናቡን በአግባቡ ይቀበላል። ብዙ ግጦሽና ዕፀዋትም ያበቅላል። ከፊሉ ደግሞ ውሃ የማያሰርፅ ደረቅ ይሆንና ውሃውን ቋጥሮ ይይዛል። አላህም በዚህ ውሃ ሰዎችን ይጠቅምበታል። ሰዎች ከርሱ ይጠጣሉ። ከፊሉ መሬት ደግሞ ውሃ የማይቋጥር፤ ግጦሽም የማያበቅል አሸዋማ ይሆናል። የነዚህ መሬቶች ምሳሌ የመጀመሪያው የአላህን ሃይማኖት የተረዳ፤ አላህ በኔ አማካኝነት የላከው ቅን መመሪያ የተጠቀመውና እርሱን አውቆ ያሳወቀው ሰው ምሳሌ ነው። ሁለተኛው የአላህን ሃይማኖት አውቆ የሸሸው ሰው ምሳሌ ነው። ሶስተኛው እኔ የተላኩበትን የአላህን ቅን መመሪያ ያላወቀና ያልተቀበለው ሰው ምሳሌ ነው»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከኔ የሰማችሁትን አንዲት አንቀፅ እንኳ ብትሆን ለሌሎች አድርሱ። ከእስራኢል ልጆች አይሁድ የሰማችሁትን ብታወጉም ችግር የለውም። በኔ ላይ ሆን ብሎ የዋሸ ሰው በእሳት ውስጥ መቀመጫውን ያመቻች ነው።» ብለዋል።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ወደ ቅን ጎዳና የጠራ፤ የተከተሉት ሰዎች ሁሉ የሚያገኙትን ያህል ምንዳ ያገኛል። ይህም ሲሆን ከነርሱ ምንዳ ቅንጣታክል ሳይጎድል ነው።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተከታዩን ሲናገሩ ሰምቻለሁ በማለት አስተላልፈዋል፡- «ይህች ዓለም የተረገመች ናት። አላህን ግን ማስታወስና የርሱ ባለቤቶች፤ እንደዚሁም ተማሪ ወይም አስተማሪ ሲቀሩ። በውስጧ ያሉ ነገሮችም የተረገሙ ናቸው»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «እውቀትን ፍለጋ ጉዞ የወጣ ወደ ቤቱ እስኪመለስ ድረስ በአላህ መንገድ ጂሃድ ላይ ነው»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ሙእሚን ፍፃሜው ጀነት እስኪሆን ድረስ ከበጎ ነገር አይጠግብም።»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አሊም በአምላክ ላይ ያለው ብልጫ እኔ ከናንተ መካከል በደረጃ ዝቅተኛ በሆነው ላይ ያለብኝ ብልጫ ያህል ነው»

በመቀጠልም የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ፡- «አላህና መላኢኮች፤ የሰማያትና የምድር ነዋሪዎች፤ ሌላው ቀርቶ ከጉድጓድ ውስጥ ያለች ጉብደንና ከባህር ውስጥ ያለ ዓሳ እንኳ ሰዎችን በጎ ነገር ለሚያስምር ነው ሶለዋት ያወርዱታል»

አቡ ዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዳች እውቀት ተጠይቆ የደበቀ በዕለተ ቂያማ በእሳት ልጓም ይለጎማል።»

አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህን ውዴታ በመሻት የሚከጅልን እውቀት ለዓለማዊ ዓላማ ሲል የተማረ በዕለተ ቂያማ የጀነትን ሽታ አያገኝም።»

✶4 አስተዋዩች እንጂ ፈሪዎች እንዳልሆናችሁ እንዲረዱ አድርጓቸው ማለት ነው።

ከንስሓ መግባት ምዕራፍ **(122)** ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በተቡክ ዘመቻ የአስመሳዮችን ችግር በማጋለጥ ከፍተኛ ስራ ሲሰሩ ሙስሊሞች በበኩላቸው ከዚህ በኋላ ነብዩ በሚዘምቱበትም ሆነ በሚያዘምቱበት የዘመቻ አይነት በአንዱም አንቀርም አሉ። ከተቡክ ዘመቻ እንደተመለሱ ወደ አንዲት ዘመቻ አንድ የጦር ክፍል ለመላክ ሰዎችን መመልመል ሲጀምሩ ሁሉም እንሄዳለን በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍከ (113-122) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በአላህ በማጋራት ወንጀል ተዘፍቆ ለሞተ ሰው ምህረትን መለመን ለሟቹ የሚሰጠው ምንም አይነት ፋይዳ የሌለው መሆኑን፤
2. ለዚህ አይነቱ ሙሽሪክ ሟች ምህረት መለመን የተከለከ ስለመሆኑ፤
3. በቃል መገኘት ቃልን በተገቢው መልኩ መሙላት ግዴታ ስለመሆኑ፤
4. አላህ ለሰው ልጆች እውነቱን ሳያሳያቸውና መልካሙን ጎዳና ሳያመለክታቸው ማስረጃ ሳያቆምባቸው ጠማማዎች ናችሁ የማይል ጌታ መሆኑን፤
5. የነብዩ (ﷺ) ሙሐመድን አጎት አቡጣሊብ ኢስላምን እንዳልተቀበሉና ተቀብለዋል እየተባለ የሚወራውና እስከ መፅሀፍ ድረስ የተደረሰበት ጉዳይ ስህተት ስለመሆኑ፤
6. ነብዩ (ﷺ) አጎታቸው አቡ ጧሊብ ኢስላምን እንዲቀበሉ የነበራቸውን ከፍተኛ ጉጉት፤
7. የአንድ ተግባር ጠቀሜታው መቋጫው ሲያምር ብቻ መሆኑን፤
8. እነዚህ ሰዎች በዚሁ በመጨረሻ ሰዓትም ቢሆን ላኢላሀ ኢለሏህ ብለው ቢሆን ኖሮ ከእሳት ነፃ ይሆኑ እንደነበር፤
9. መጥፎ ጓደኛ ሊያደርስ የሚችለው ጉዳት እስከምን ድረስ እንደሆነ፤
10. ለቅድመ አባቶች የሚሰጠው ክብር ከመጠን በላይ መሆኑ የሚያስከትለው ጥፋት ምን እንደሚመስል፤
11. ነብዩ (ﷺ) አንኳን ቢሆኑ ከተሳሳቱ ተቀባይነት እንደሌላቸው ስለ አጎታቸው ምህረት መለመን መከልከላቸው አንዱ ምሳሌ መሆኑን፤
12. ነብዩ (ﷺ) በኢጅቲሃድ የሰሩና ከዚያም አላህ ይመልሳቸው እንደነበር፤
13. ከአላህ ጓዶች ምን ያህል ታላቅ ክብርና ማዕረግ የተሰጣቸው የአላህ ታማኝና ቅን አገልጋይ እንደነበሩ፤
14. የተቡክ ዘመቻ ታሪካዊ ሂደትና ይዘት ምን መልክ እንደነበረው ትክክለኛ ቁርአናዊ ትረካ፤
15. በዚህ የጭንቅ ዘመቻ ወቅት ዘመቻ አላህ ለሙዕሚኖች ፅናትን በመስጠትና ቆራጥነትን በማላባስ የዋለላቸውን መጠነ ሰፊ ውለታ፤
16. እውነትን በመናገር ስህተታቸውን በማመን በንፁህ ልቦና ረሱል ሙሐመድን (ﷺ) የቀረቡት ከዕብ ኢብኑ ማሊክና ጓደኞቹ እጅግ ከፋ ያለ ክብርና ማዕረግ እንዲሁም የአላህን ምህረት ማግኘታቸውን፤
17. የራስን ሕይወት ጨምሮ ሌሎች መልካም ነገሮችን በሙሉ ከረሱል ሙሐመድ (ﷺ) በታች እንጂ ከእርሳቸው ጋር በእኩል ደረጃም ሆነ አስበልጦ መውደድ የተከለከለ ነው። ረሱል ሙሐመድ (ﷺ) ከሁሉም ነገር በላይ ማስበለጥ ግዴታ መሆኑን፤
18. የአላህን ሃይማኖት ለመርዳትና ለማስፋፋት ብሎም ለኢስላም ተብለው የሚደረጉ ጉዞዎች ያላቸው ምንዳ ከፍተኛ መሆኑን፤
19. እውቀትን መፈለግ በአላህ መንገድ ላይ ከመታገል ከጂሃድ ጋር እኩል የሆነ ምንዳ የሚያስገኝ እጅግ የተቀደሰ ተግባር ስለመሆኑ፤
20. የሙስሊሙን ህብረተሰብ ህልውና የሚያስከብሩ ታጋዮች እንደሚያስፈልጉ ሁሉ የሙስሊሙን ህይወት በእውቀት ፈር የሚያስይዙ ሃይማኖታዊ ትምህርቶችን የሚሰጡ፤ ብይኖችን የሚያስተላልፉ በ እውቀት የታነፁ አዋቂዎች (ምሁራን) የሚያስፈልጉ ስለመሆኑ፤
21. ስለ እውቀት በተለይም ፊቅህ ያለውን ከፍተኛ ማዕረግ፤
22. ያወቀ ሰው ያላወቀን ማሳወቅ እንዳለበት፤

23. ሙስሊሞች እያንዳንዱን የታወቁት የትምህርት አይነቶች ሁሉ የሚሸፍን አካል ማዘጋጀትና ማመቻቸት እንዳለባቸው፤
24. የሰው ልጆች ከሚመኙት ሁሉ ትልቁና የአላህን ይቅርታ ማግኘት መሆኑን፤
25. አላህ ለሰው ልጆች ይቅርታ የሚለው በፀፀታቸው ልክ መሆኑን እንማራለን።

وَإِذَا مَآ أُنزِلَتۡ سُورَةٞ فَمِنۡهُم مَّن يَقُولُ أَيُّكُمۡ زَادَتۡهُ هَٰذِهِۦٓ إِيمَٰنٗاۚ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ
فَزَادَتۡهُمۡ إِيمَٰنٗا وَهُمۡ يَسۡتَبۡشِرُونَ ١٢٤ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٞ فَزَادَتۡهُمۡ رِجۡسًا إِلَىٰ
رِجۡسِهِمۡ وَمَاتُواْ وَهُمۡ كَٰفِرُونَ ١٢٥ أَوَلَا يَرَوۡنَ أَنَّهُمۡ يُفۡتَنُونَ فِي كُلِّ عَامٖ مَّرَّةً أَوۡ مَرَّتَيۡنِ
ثُمَّ لَا يَتُوبُونَ وَلَا هُمۡ يَذَّكَّرُونَ ١٢٦ وَإِذَا مَآ أُنزِلَتۡ سُورَةٞ نَّظَرَ بَعۡضُهُمۡ إِلَىٰ بَعۡضٍ هَلۡ
يَرَىٰكُم مِّنۡ أَحَدٖ ثُمَّ ٱنصَرَفُواْۚ صَرَفَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُم بِأَنَّهُمۡ قَوۡمٞ لَّا يَفۡقَهُونَ ١٢٧

**124-127.** ምእራፍ በተወረደ ጊዜ ከመናፍቃን ውስጥ ማንኛችሁ ነው? ይህ ምእራፍ እምነትን የጨመረለት የሚል ሰው አለ። እነዚያ ያመኑት ሰዎች የሚደሰቱ ሲሆኑ እምነትን ጨመረላቸው። እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ከፍሎች ግን በርክሰታቸው ላይ እርክሰትን ጨመረላቸው። እነርሱም ከሓዲያን ሆነው ሞቱ። በየዓመቱ አንድ ወይም ሁለት ጊዜ እነርሱ የሚሞከሩ መሆናቸውን አያዩምን? ከዚያ አይፀፀቱምን?እነርሱም አይገሰፁምን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱን የሚያወሳ ምእራፍም በተወረደ ጊዜ አንድ ሰው ያያችኋልን? እያሉ ከፊሎቻቸው ወደ ከፊሉ ይመለከታሉ። ከዚያ ተደብቀው ይሄዳሉ። እነርሱ የማያውቁ ህዝቦች በመሆናቸው አላህ ልቦቻቸውን አዞረ።

لَقَدۡ جَآءَكُمۡ رَسُولٞ مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ عَزِيزٌ عَلَيۡهِ مَا عَنِتُّمۡ حَرِيصٌ عَلَيۡكُم
بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ رَءُوفٞ رَّحِيمٞ ١٢٨

**128.** (ሰዎች ሆይ!) ከጎሳችሁ ውስጥ የሆነ መቸገራችሁ በእርሱ ላይ ከባድ ጉዳይ የሆነበት እናንተ እምነት እንዲኖራችሁ በጣም የሚጓጓ በምእምናን ላይ ሩህሩህና አዛኝ የሆነ መልዕክተኛ በእርግጥ መጣላችሁ።

فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَقُلۡ حَسۡبِيَ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ عَلَيۡهِ تَوَكَّلۡتُۖ وَهُوَ رَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡعَظِيمِ ١٢٩

**129.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢያፈገፍጉ አላህ በቂዬ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። በእርሱ ላይ ብቻ ተመካሁ። እርሱም የታላቁ ዐርሽ ጌታ ነው በላቸው።

**ከንስሓ መግባት ምዕራፍ ከአንቀፅ (123-129) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፤.**

1. በምድር ላይ የኢስላምን ብርሃን ለማደብዘዝ የሚሞክሩ ሙስሊሙን የሚፈታተኑ ፀረ. ኢስላም ኃይላት አፍራሽ እንቅስቃሴ እስካለ ድረስ (ሸርጡ) መስፈርቱ የተሟላ ጂሀድ ምን ጊዜም የማይቀር ስለመሆኑ፤
2. አላህ ለእርሱ ቅን አገልጋዮች የሆኑት በሙሉ እንደሚረዳቸው ድልን እንደሚሰጣቸው ቃል መግባቱን፤
3. እምነት እንደሁኔታው የሚጨምርና የሚቀንስ ስለመሆኑ፤
4. በመልካም ስራዎች ሰዎች ልባቸውን በደስታ መሙላትና ሀሴት ማድረጋቸው ተገቢ መሆኑን፤
5. ቀልቡ በክህደትና በወንጀል በሽታ የተበከለ ሰው፤ ኃጢአቱን ካልተወ የቀልቡ በሽታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ እንደሚመጣና በአንፃሩ ጤናማ የሆነ፤ በእምነትና በመልካም ስራዎች ውዴታ የተሞላ ልብ ያለውና አማኝ ከጊዜ ወደ ጊዜ ልቡ ለእምነት ክፍት፤ ለአላህም ታዛዥ እየሆነ እንደሚመጣ፤
6. የመናፍቃንን ውስጣዊ ክህደት የሚያጋልጥ ቁርአናዊ አንቀፅ ተስተምህሮ እንዳለ፤
7. አላህ አስተማሪ የሆነ ነብይ በመላክ ለዚህ ሕዝብ ታላቅ የሆነ ውለታን የዋለ ስለ መሆኑ፤
8. የታላቁ ነብዩ (ﷺ) ምሉዕ ባህሪያትና መልካም ስብዕና፤
9. በአላህ ብቻ መመካት ያለውን ፋይዳና ተገቢነት፤
10. የአላህ ዐርሽ ታላቅነት እንማራለን።

የንስሓ መግባት ምዕራፍ እዚህ ላይ በአላህ ፍቃድ አበቃ።

# ምዕራፍ (10)
# የነብዩ ዩኑስ ምዕራፍ
# (ሱረቱ ዩኑስ)

سُورَةُ يُونُس

## በመካ ወረደ። አናቅፅ (109) ናቸው።
## የሱረቱ ዩኑስ መግቢያ

ይህን ስያሜ ያገኘው በ (98) ኛው አንቀፅ ላይ ታሪካቸው በተወሱት ነብይ ስም ነው የተሰየመው። ይህ ነብይ በቁርኣን ውስጥ አራት ጊዜ ተወስቷል።

በሴቶች ምዕራፍ በ (163) ኛው፤ በእንስሳዎች ምዕራፍበ (86) ኛው፤ በዩኑስ ምዕራፍበ (98) ኛው፤ በሷፋት ምዕራፍ (139) ኛ አናቅፅ ላይ ነው። በአንቢያእ ምዕራፍም (87-88) ባሉት ተወስቷል። ይህ ነብይ የነበሩበት ሀገር በዘመኑ ቱኒስ ተብሎ የሚታወቀው ሀገር ሲሆን በኋላ ዳሞሲል አጠገብ ወደ ምትገኘው ኒኒዋ ሰፈር ሄዱ።

ሲጀምር የቁርኣንን ትልቅነት በማሳየት ነው። በማስከተልም ከሓዲያን ስለ ነብዩ (ﷺ) የሚሉትን፤ ይህን ዓለምና አላህ በዚህ ዓለም ውስጥ የፈጠረውን አምር በማውሳት ነው። ስለቂያማ ቀን ምንዳም ከሐዲያንን በተመለከተ አላህ ያስቀመጠውን ነገር ያወሳል። እነርሱንም በእምንነታቸው ያወግዛል። ሰዎች በችግርም ጊዜ ሆነ በደስታ ወቅት እንዴት እንደሚሆኑ፤ አላህ ብዙ ነገሮችን እንደሚችል፤ ጣኦታት ደግሞ ምንንም እንደማይችሉ ከየትም ቀጣጥፈውም ቢሆን አንዲት የቁርኣንን ምዕራፍ የምትመስል ለማምጣት እንዲሞክሩ ይጋብዛል። ሰዎች ይህን ሁሉ አይተውና ሰምተው ካላመኑ የአላህ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው ይዘረዝራል። ከዚያ ነብዩን (ﷺ) ማጽናናት የሚያስችሉ የኑህ፤ የሙሳንና የሐሩንን፤ የዩኑስን ታሪክ በማውሳት ተልዕኮውን ያጠቃልላል። ይህ ምዕራፍ ከመካዊ ምእራፎች አንዱ ነው። የሚያተኩርበት ዋናው ነጥብም ተውሂድን በተመለከተ ነው። በተለይ በአላህ በነብያችን ሙሐመድ (ﷺ) በመጽሐፍትና በሙቶ በመነሳት ላይ ከፍተኛ መግለጫ ይሰጣል። ሸሪዓን አጥብቆ መያዝ እንደሚገባ ጥብቅ ትዕዛዝ ይሰጣል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓرۚ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡحَكِيمِ ١

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ራ፤*። ይህ በውስጥ የተወሳው ጥበብ የተሞላው መጽሐፍ አንቀፆች አካል ነው።

✷ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

أَكَانَ لِلنَّاسِ عَجَبًا أَنۡ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ رَجُلٖ مِّنۡهُمۡ أَنۡ أَنذِرِ ٱلنَّاسَ وَبَشِّرِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَنَّ لَهُمۡ قَدَمَ صِدۡقٍ عِندَ رَبِّهِمۡۗ قَالَ ٱلۡكَٰفِرُونَ إِنَّ هَٰذَا لَسَٰحِرٞ مُّبِينٌ ٢

**2.** *(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲ ሰዎችን አስፈራራ (አስጠንቅቅ)፤ እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ደግሞ ከጌታቸው ዘንድ መልካም ምንዳ ያላቸው መሆኑን አብስር በማለት ከእነርሱ መካከል ወደ ሆነ አንድ ሰው ራዕይን ማውረዳችን ለሰዎች ድንቅ ሆነባቸውን? ከሓዲያን ይህ ሰው ግልጽ ድግምተኛ ነው አሉ።

✷ ከዩኑስ (2) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አላህ ነብዩን (ﷺ) መልዕክተኛ አድርጎ በላከ ጊዜ ካፊሮቹ «አላህ ሠውን» ማለትም «እንደ ሙሐመድ ያለውን መልዕክተኛ አድርጎ ከመላክ የፀዳ ነው» በማለታቸው ምክንያት ይህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ፤ ኢብኑ አልጀውዚ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِنَّ رَبَّكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٖ ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَۖ مَا مِن شَفِيعٍ إِلَّا مِنۢ بَعۡدِ إِذۡنِهِۦۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ٣ إِلَيۡهِ مَرۡجِعُكُمۡ جَمِيعٗاۖ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقًّاۚ إِنَّهُۥ يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ لِيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ بِٱلۡقِسۡطِۚ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَهُمۡ شَرَابٞ مِّنۡ حَمِيمٖ وَعَذَابٌ أَلِيمُۢ بِمَا كَانُواْ يَكۡفُرُونَ ٤

**3-4.** ጌታችሁ ያ! ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ውስጥ ብቻ የፈጠራቸው አላህ ነው። ከዚያ ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብር ሲሆን በዐርሹ ላይ ከፍ አለ*። ከእርሱ በጎ ፈቃድ በኋላ ቢሆን እንጂ አንድም አማላጅ የለም። ይህ አላህ ጌታችሁ ነው። እናም በትክክል ተገዙት። አትገሰፁምን? (ሰዎች ሆይ!) የሁላችሁም መመለሻችሁ ወደ እርሱ ብቻ ነው። ይህም የተረጋገጠ የአላህ ቃል ኪዳን ነው። እርሱ መፍጠርን ይጀምራል። ከዚያ እነዚያ ያመኑትንና

መልካም የሠሩትን ሰዎች በትክክል ይመነዳ ዘንድ ፍጡራንን ከሞት በኋላ ህያው ያደርጋል። እነዚያ የካዱት ግን በክህደታቸው ምክንያት የፈላ ውሃ መጠጥና አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

✴ ይህንና መሰሎቹ አናቅፅ በተመለከተ በአል አዕራፍ በ (54) ኛው አንቀፅ ላይ የተሰጠውን ሰፊ ማብራሪያ ተመልከቱ።

هُوَ ٱلَّذِي جَعَلَ ٱلشَّمۡسَ ضِيَآءٗ وَٱلۡقَمَرَ نُورٗا وَقَدَّرَهُۥ مَنَازِلَ لِتَعۡلَمُواْ عَدَدَ ٱلسِّنِينَ
وَٱلۡحِسَابَۚ مَا خَلَقَ ٱللَّهُ ذَٰلِكَ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۚ يُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لِقَوۡمٖ يَعۡلَمُونَ ٥

**5.** እርሱ ያ ፀሐይን አንፀባራቂ ጨረቃንም አብሪ ያደረገ፤ የዓመታትን ቁጥርና ሒሳብን ታውቁ ዘንድም ለጨረቃ የተለያዩ መስፈሪያ እርከኖችን የወሰነ ነው። አላህ ይህንን በእውነት እንጂ በከንቱ አልፈጠረውም። ለሚያውቁ ሕዝቦችም አያሌ አንቀፆችን ያብራራል።

إِنَّ فِي ٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَمَا خَلَقَ ٱللَّهُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَّقُونَ ٦

**6.** ሌሊትና ቀን በመተካካታቸው አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ በፈጠረው ሁሉ ለሚጠነቀቁ ሕዝቦች ታላላቅ ተአምራት አሉ።

**ከዩኑስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-6) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የነብዩን (ﷺ) እውነተኛ ነብይነትና በእርሳቸው ላይ ይወረዱ የነበሩ የአላህ ወህዮች ሐቅ መሆናቸውን፤
2. የነብዩ (ﷺ) አብይ ተልእኮ ሰዎችን በገነት እያበሰሩና ከገሀነም እሳት እያስፈራሩ ማስተማር ስለመሆኑ፤
3. የአላህን ብቸኛ አምላክነት ማረጋገጥና እውነተኛ አምላክነት ለእርሱ ብቻ ስለመሆኑ፤
4. አላህ በሁሉ ነገር ብቸኛ አስተናባሪ መሆኑን፤
5. ሙቶ መነሳትና እንደየስራው ምንዳ ማግኘት ሐቅ መሆኑን፤
6. ፀሐይና ጨረቃ ለምን አላማ እንደተፈጠሩና የሚሰጡት አገልግሎት ምን ምን እንደሆነ፤
7. የሒሳብ፤ የስነ ፈለግና የካላንደር ማወቂያ ትምህርት አስፈላጊነቱ የጎላ ስለመሆኑና ባጠቃላይ ደግሞ በማንኛውም ዘርፍ ዕውቀት ተፈላጊ ነው ስለመሆኑ የሚሉት ናቸው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا وَرَضُواْ بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَٱطۡمَأَنُّواْ بِهَا وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِنَا
غَٰفِلُونَ ٧ أُوْلَٰٓئِكَ مَأۡوَىٰهُمُ ٱلنَّارُ بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٨

**7-8.** እነዚያ ከኛ ጋር መገናኘታቸውን የማይፈሩ ቅርቢቱን ሕይወት የወደዱና በእሷም የረኩ እነርሱ ከአንቀፆቻችን ዘንጊዎች የሆኑትን። እነዚያ ይሠሩት በነበሩት ኃጢአት ምክንያት መኖሪያቸው በእሳት ውስጥ ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ يَهۡدِيهِمۡ رَبُّهُم بِإِيمَٰنِهِمۡۖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهِمُ ٱلۡأَنۡهَٰرُ فِي
جَنَّٰتِ ٱلنَّعِيمِ ٩ دَعۡوَىٰهُمۡ فِيهَا سُبۡحَٰنَكَ ٱللَّهُمَّ وَتَحِيَّتُهُمۡ فِيهَا سَلَٰمٞۚ وَءَاخِرُ دَعۡوَىٰهُمۡ أَنِ
ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٠

**9-10.** እነዚያ በአላህ ያመኑትና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ሰዎች ሁሉ ጌታቸው በእምነታቸው ምክንያት የገነትን መንገድ ይመራቸዋል። ከሥሮቻቸው ወንዞች ይፈስሳሉ። በመጠቀሚያ ገነቶች ውስጥም ዝንታለም ይኖራሉ። በእርሷም ውስጥ ፀሎታቸው የሚሆነው ጌታችን ሆይ! ጥራት ይገባህ ማለት ብቻ ነው። በእርሷ ውስጥ መከባበሪያቸው ሰላም መባባል ነው። የመጨረሻ ፀሎታቸውም ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይገባው። (ማለት) ነው

۞وَلَوۡ يُعَجِّلُ ٱللَّهُ لِلنَّاسِ ٱلشَّرَّ ٱسۡتِعۡجَالَهُم بِٱلۡخَيۡرِ لَقُضِيَ إِلَيۡهِمۡ أَجَلُهُمۡۖ
فَنَذَرُ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا فِي طُغۡيَٰنِهِمۡ يَعۡمَهُونَ ١١

**11.** አላህ ለሰዎች ደግን ነገር ለማግኘት እንደ መቻኮላቸው የሚጠይቁትንም ክፉን ነገር ቢያቻኩልባቸው ኖሮ በዚያችው ጊዜያቸው እድሜያቸው በተፈፀመ ነበር። እነዚያን መገናኘታችንን የማይከጅሉ ሰዎች በጥመታቸው ውስጥ እየዋለሉ እንተዋቸዋለን።

وَإِذَا مَسَّ ٱلۡإِنسَٰنَ ٱلضُّرُّ دَعَانَا لِجَنۢبِهِۦٓ أَوۡ قَاعِدًا أَوۡ قَآئِمٗا فَلَمَّا كَشَفۡنَا عَنۡهُ ضُرَّهُۥ مَرَّ
كَأَن لَّمۡ يَدۡعُنَآ إِلَىٰ ضُرّٖ مَّسَّهُۥۚ كَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِلۡمُسۡرِفِينَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٢

**12.** የሰውን ልጅ ጉዳት ባገኘው ጊዜ በጎኑ ላይ ተጋድሞ ወይም ተቀምጦ ወይም ቆሞ ይለምንና ጉዳቱን ከእሱ ላይ በገለጥንለት ጊዜ ወደ አገኘው ጉዳት እንዳልተማፀነን ሆኖ ያልፋል። ልክ እንደዚሁ ለድንበር አላፊዎች ሁሉ ይሠሩት የነበሩት መጥፎ ሥራ ተሸለመላቸው።

وَلَقَدۡ أَهۡلَكۡنَا ٱلۡقُرُونَ مِن قَبۡلِكُمۡ لَمَّا ظَلَمُواْ وَجَآءَتۡهُمۡ رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ وَمَا كَانُواْ
لِيُؤۡمِنُواْۚ كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ١٣ ثُمَّ جَعَلۡنَٰكُمۡ خَلَٰٓئِفَ فِي ٱلۡأَرۡضِ مِنۢ بَعۡدِهِمۡ
لِنَنظُرَ كَيۡفَ تَعۡمَلُونَ ١٤ وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَاتُنَا بَيِّنَٰتٖ قَالَ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا
ٱئۡتِ بِقُرۡءَانٍ غَيۡرِ هَٰذَآ أَوۡ بَدِّلۡهُۚ قُلۡ مَا يَكُونُ لِيٓ أَنۡ أُبَدِّلَهُۥ مِن تِلۡقَآيِٕ نَفۡسِيٓۖ إِنۡ أَتَّبِعُ إِلَّا

مَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّۖ إِنِّيٓ أَخَافُ إِنۡ عَصَيۡتُ رَبِّي عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ﴿١٥﴾ قُل لَّوۡ شَآءَ ٱللَّهُ مَا تَلَوۡتُهُۥ
عَلَيۡكُمۡ وَلَآ أَدۡرَىٰكُم بِهِۦۖ فَقَدۡ لَبِثۡتُ فِيكُمۡ عُمُرٗا مِّن قَبۡلِهِۦٓۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴿١٦﴾ فَمَنۡ
أَظۡلَمُ مِمَّنِ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوۡ كَذَّبَ بِـَٔايَٰتِهِۦٓۚ إِنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلۡمُجۡرِمُونَ ﴿١٧﴾

**13-17.** ከናንተ በፊት የነበሩትን የብዙ ክፍለ ዘመናት ሰዎች መልዕክተኞቻቸው በማስረጃዎች የመጡላቸው ሲሆኑ በበደሉና የማያምኑም በሆኑ ጊዜ በእርግጥ አጠፋናቸው፡፡ ልክ እንደዚሁ ተንኮለኞችን ህዝቦች እንቀጣለን፡፡ (ሰዎች ሆይ!) ከዚያ እንዴት እንደምትሠሩ ልንመለከት ከእነርሱ በኋላ በምድር ላይ ምትኮች አደረግናችሁ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንቀፆቻችን ግልጽ ሆነው በእነርሱ ላይ በተነበቡላቸው ጊዜ እነዚያ መገናኘታችንን የማይፈሩት (የማይሹት) ሰዎች ከዚህ ሌላ የሆነን ቁርኣን አምጣልን ወይም ለውጠው ይላሉ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ ከራሴ በኩል ልለውጠው አይገባኝም፡፡ ወደ እኔ የሚወረደውን እንጂ አልከተልም፡፡ እኔ በጌታዬ ትዕዛዝ ላይ ባምጽ የታላቅን ቀን ቅጣት እፈራለሁ በላቸው፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! አላህ በሻ ኖሮ በእናንተ ላይ ባላነበብኩትና አላህ እርሱን ባላሳወቃችሁ ነበር፡፡ በእናንተም ውስጥ ከእርሱ በፊት (ምንም ሳልል) ብዙን እድሜ በእርግጥ ኖሬያለሁ፡፡ ይህን አታውቁምን? በላቸው፡፡ በአላህ ላይ እብለትን ከቀጣጠፈ ወይም በአንቀጾቹ ከአስተባበለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው? እነሆ አመፀኞች አይድኑም፡፡

ከዩኑስ ምዕራፍ (15) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ መሪዎች የነበሩ ከሓዲያን እንድናምንልህ ከፈለግህ ከዚህ ሌላ የሆነ ቁርኣን አምጣ ብለው በመጠየቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ዋሒዲ)

وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُمۡ وَلَا يَنفَعُهُمۡ وَيَقُولُونَ هَٰٓؤُلَآءِ شُفَعَٰٓؤُنَا عِندَ ٱللَّهِۚ قُلۡ
أَتُنَبِّـُٔونَ ٱللَّهَ بِمَا لَا يَعۡلَمُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿١٨﴾

**18.** አጋሪዎች ከአላህ ሌላ የማይጎዳቸውንና የማይጠቅማቸውን ይገዛሉ፡፡ እነዚህ ከአላህ ዘንድ አማላጆቻችን ናቸው ይላሉ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ እናንተ ትነግሩታላችሁን? በላቸው፡፡ አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ፡፡ ላቀም፡፡

وَمَا كَانَ ٱلنَّاسُ إِلَّآ أُمَّةً وَٰحِدَةً فَٱخْتَلَفُوا۟ ۚ وَلَوْلَا كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ لَقُضِىَ بَيْنَهُمْ
فِيمَا فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ١٩ وَيَقُولُونَ لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْهِ ءَايَةٌ مِّن رَّبِّهِۦ ۖ فَقُلْ إِنَّمَا ٱلْغَيْبُ لِلَّهِ
فَٱنتَظِرُوٓا۟ إِنِّى مَعَكُم مِّنَ ٱلْمُنتَظِرِينَ ٢٠ وَإِذَآ أَذَقْنَا ٱلنَّاسَ رَحْمَةً مِّنۢ بَعْدِ ضَرَّآءَ مَسَّتْهُمْ
إِذَا لَهُم مَّكْرٌ فِىٓ ءَايَاتِنَا ۚ قُلِ ٱللَّهُ أَسْرَعُ مَكْرًا ۚ إِنَّ رُسُلَنَا يَكْتُبُونَ مَا تَمْكُرُونَ ٢١

**19-21.** ሰዎች አንድ ህዝብ እንጂ ሌላ አልነበሩም።* ከዚያ ተለያዩ። ከጌታህ ያለፈ ቃልም ባልነበረ ኖሮ በዚያ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው በቶሎ በተፈረደ ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርሱ ላይም ከጌታው የሆነች ተአምር ለምን አትወረድለትም ይላሉ። ሩቅ ነገር ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። እናንተም ተጠባበቁ እኔም ከናንተው ጋር ከሚጠባበቁት ነኝና በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎች ካገኛቸው ጉዳት በኋላ እዝነትን (ምቾትን) ባቀመስናቸው ጊዜ ወዲያውኑ ለእነርሱ በተአምራቶቻችን በማላገጥ ተንኮል ይኖራቸዋል። አላህ ቅጣቱ ፈጣን ነው። መልዕክተኞቻችን የምትመክሩትን ነገር ሁሉ በእርግጥ ይጽፋሉ በላቸው።

* ይህ አንድነት የእምነት አንድነት ማለት ነው። ይህን አስመልክተው የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «ሁሉም ህፃን በኢስላም ላይ ሆኖ ይወለዳል። ነገር ግን ወላጆቹ ወደ አይሁዳዊነት ወይም ወደ ክርስትና ወይም ወደ ጣኦት አምላኪነት ይቀይሩታል። ይህም ልክ ጤንነቱ ሙሉ እንደሆነ እንስሳ አይነት ነው። በዚህ እንስሳ ላይ እንከን ታገኛላችሁን።»

هُوَ ٱلَّذِى يُسَيِّرُكُمْ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ ۖ حَتَّىٰٓ إِذَا كُنتُمْ فِى ٱلْفُلْكِ وَجَرَيْنَ بِهِم بِرِيحٍ طَيِّبَةٍ
وَفَرِحُوا۟ بِهَا جَآءَتْهَا رِيحٌ عَاصِفٌ وَجَآءَهُمُ ٱلْمَوْجُ مِن كُلِّ مَكَانٍ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُمْ أُحِيطَ بِهِمْ
دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ لَئِنْ أَنجَيْتَنَا مِنْ هَٰذِهِۦ لَنَكُونَنَّ مِنَ ٱلشَّٰكِرِينَ ٢٢ فَلَمَّآ
أَنجَىٰهُمْ إِذَا هُمْ يَبْغُونَ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ ۗ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّمَا بَغْيُكُمْ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُم ۖ
مَّتَٰعَ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ ثُمَّ إِلَيْنَا مَرْجِعُكُمْ فَنُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ٢٣

**22-23.** (ሰዎች ሆይ!) እርሱ (አላህ) ያ በየብስና በባሕር የሚያስኬዳችሁ ነው። በመርከቦችም ውስጥ በሆናችሁና በእነርሱም በመልካም ነፋስ በእርሷ የተደሰቱ ሆነው መርከቦቹ በተንሻለሉ ጊዜ ሀይለኛ ነፋስ ትመጣባታለች። ከየስፍራውም ማዕበል ይመጣባቸዋል። እነርሱም ለጥፋት የተከበቡ መሆናቸውን ያረጋግጣሉ ያን ጊዜ አላህን ከዚህች (ጭንቀት) ብታድነን በእርግጥ ከአመስጋኞቹ እንሆናለን ሲሉ እምነታቸውን ለእርሱ ብቻ ፍፁም

አድርገው ይለምኑታል። በአዳናቸውም ጊዜ እነርሱ ወዲያውኑ ያለ አግባብ በምድር ላይ ወሰን ያልፋሉ። እናንተ ሰዎች ሆይ ወሰን ማለፋችሁ ጥፋቱ በነፍሶቻችሁ ላይ ብቻ ነው። እርሱ የቅርቢቱ ህይወት መጠቀሚያ ነው። ከዚያ መመለሻችሁ ወደ እኛ ነው። ትሠሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እንነግራችኋለን።

إِنَّمَا مَثَلُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا كَمَآءٍ أَنزَلْنَٰهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَٱخْتَلَطَ بِهِۦ نَبَاتُ ٱلْأَرْضِ مِمَّا يَأْكُلُ ٱلنَّاسُ وَٱلْأَنْعَٰمُ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَخَذَتِ ٱلْأَرْضُ زُخْرُفَهَا وَٱزَّيَّنَتْ وَظَنَّ أَهْلُهَآ أَنَّهُمْ قَٰدِرُونَ عَلَيْهَآ أَتَىٰهَآ أَمْرُنَا لَيْلًا أَوْ نَهَارًا فَجَعَلْنَٰهَا حَصِيدًا كَأَن لَّمْ تَغْنَ بِٱلْأَمْسِ ۚ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ لِقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٢٤﴾ وَٱللَّهُ يَدْعُوٓا۟ إِلَىٰ دَارِ ٱلسَّلَٰمِ وَيَهْدِى مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٢٥﴾

**24-25.** የቅርቢቱ ህይወት ምሳሌ ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ በእርሱም ሰውና እንስሳዎች ከሚበሉት የምድር በቃይ ተቀላቅሎበት እንደፋፋ ምድርም ውበትዋን በያዘችና ባጌጠች ጊዜ ባለቤቶችዋን በእርሷ ላይ እነርሱ ቻዮች መሆናቸውን ባሰቡ ጊዜ ትዕዛዛችን ሌሊት ወይም ቀን መጥቶባት ትላንት እንዳልነበረች የታጨደች እንዳደረግናት ብጤ ነው። ልክ እንደዚሁ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ሁሉ አንቀፆችን እናብራራለን። አላህ ሁል ጊዜም ወደ ሰላም አገር ይጠራል። የሚፈልገዉን ሰውም ወደ ቀጥተኛው መንገድ ይመራል።

**ከዩኑስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (7-25) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መጪውን ዘለአለማዊ የአኼራ ሕይወት በመዘንጋት በምድራዊ ሕይወት ጉጉት መዋጥ የተጠላ መሆኑንና ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ፤
2. የአላህን ፍጡራን አፈጣጠርና አኗኗር እንዲሁም የቁርኣን አናቅፅን ባለማስተንተን ምክንያት ከሚፈጠር መዘናጋት ጥንቃቄ መውሰድ እንደሚገባ፤
3. እምነትና መልካም ተግባር ወደ ጀነት የሚያደርሱ ዋነኛ የደስታና የተድላ በር ቁልፎች መሆናቸውን፤
4. በጀነት ውስጥ የሚገኘው ፀጋ አካላዊና መንፈሳዊ ደስታን ለዘለዓለም የሚሰጥ ፀጋ ስለ መሆኑ፤
5. የአላህ ርህራሄ በግልፅ የሚታይና እዝነቱም ሰፊ መሆኑን፤
6. ከሓዲያንን ለመቅጣት አላህ የማይቸኩል ጌታ መሆኑንና ይፀፀቱ ዘንድ ጊዜና እድል እንደሚሰጣቸው፤
7. ከሓዲያን በችግር ጊዜ አላህን እንደሚጠሩና የእርሱን እገዛ እንደሚፈልጉ፤ ችግሩ ሲለቃቸው ግን እንደማያውቁት ሆነው ወደ ነበሩበት ክህደትና ጥፋት እንደሚመለሱ፤
8. አመፀኞች ተውበት አድርገው ካልመጡ በስተቀር በዚህ ዓለምም ሆነ በአኼራው ዓለም የአላህ ቅጣት የሚጠብቃቸው መሆኑን የሚገልፅ የአላህ ዛቻ፤

9. ወንጀል ለአሰቃቂ ቅጣት የሚዳርግ መሆኑን፤
10. በሰዎች ዘንድ ቁርአን እያሰሙ ማንበብ ከጥሪ ዘዴዎች አንዱ ስለመሆኑ፤
11. የከሓዲያን ሞገድና ትዕቢት ምን እንደሚመስል፤
12. ነብዩ (ﷺ) እስከ አርባኛው ዓመት ዕድሜያቸው ድረስ ምንም እውቀት ሳይኖራቸው እንደቆዩ፤
13. በአላህ ላይ ከሚዋሽና እርሱን ከማስተባብል የበለጠና የከፋ ወንጀል ምድር ላይ የሌለ ስለመሆኑ፤
14. ከሓዲያን የሚያመልኳቸውን የሐሰት አማልክት አላህ ዘንድ ያሸማግሉናል ማለታቸው ስህተት መሆኑን፤
15. በሰዎች ዘንድ ተውሒድ (አላህን በብቸኝነት ማምለክ) መሰረታዊና ተፈጥሯዊ ፅንሰ ሃሳብ መሆኑንና ሽርክ በአላህ ላይ ማጋራት ከጊዜ በኋላ የመጣ መሰረት የሌለው የሰዎች ስሜት የወለደው ወንጀል መሆኑን፤
16. የሽርክና የተንኮል ተግባር በሰዎች መሀከል ልዩነቶችን የሚፈጥሩ መሆናቸው፤ ተውሒድ ደግሞ በሰዎች መሀከል ስምምነት የሚፈጥር መሆኑን፤
17. ግፈኞች ግፍን እያራመዱ የምድራዊ ሕይወት ቆይታቸው የሚደላደለውና ዕድሜአቸው የሚቆየው አላህ በጥበቡ ተመጣጣኝ ቅጣትን ሊሰጣቸው በማሰቡ እንደሆነ፤
18. የተሰወሩ ነገሮችን ያለ አላህ ማንም የማያውቃቸው ስለመሆኑ፤
19. ተንኮልን የሚሸርብና ሴራን የሚጎነጉንን ሁሉ አላህ ለሴራውና ለተንኮሉ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት እንደሚያከናንበው፤
20. የሰው ልጅ እጅግ ደካማና ምን ጊዜም የአላህን እርዳታ ፈላጊ የሆነ ፈጡር መሆኑን፤
21. ሰዎች በችገራቸው ጊዜ ከአላህ እገዛን መፈለጋቸውና እርሱን ብቻ መማፀናቸው ተውሒድ ተፈጥሯዊና መሰረታዊ ለመሆኑ ዋና ምስክር እንደሚሆን፤
22. በአሁኑ ወቅት ከሚታዩ አጋሪዎች ይልቅ የቀድሞ ዘመን አጋሪዎች የተሻሉ እንደነበሩና ቢያንስ በችግራቸው ጊዜ እንኳን አላህን ሙጥኝ ይሉ እንደነበር፤
23. የሰው ልጅ በሚሰራቸው ጥፋቶች ምክንያት የሚከሰቱ ቅጣቶችና አደጋዎች ገፈት ቀማሽ ራሱ ጥፋተኛው ስለ መሆኑ፤
24. ከሞት በኋላ መነሳትና የተግባርን ዋጋ ማግኘት የማይቀር ሐቅ ስለ መሆኑ፤
25. የምድራዊ ሕይወት ጊዜያዊና ኃላፊ መሆኗን የሚያሣይ ስለዱንያ ትክክለኛ ስዕል የሚሰጥ ቁርአናዊ አስተምህሮት፤
26. ከአላህ ስራዎች ላይ ማስተንተን በፍጡራኖቹ መመራመር ያለው ምንዳ ከፍ ያለ ስለመሆኑ፤
27. አላህ ለባሪያዎቹ የዋለው ውለታ መጠነ ሰፊና ብዙ መሆኑን እንማራለን።

۞ لِّلَّذِينَ أَحْسَنُواْ ٱلْحُسْنَىٰ وَزِيَادَةٌۖ وَلَا يَرْهَقُ وُجُوهَهُمْ قَتَرٌ وَلَا ذِلَّةٌۚ
أُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلْجَنَّةِۖ هُمْ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٢٦

**26.** ለእነዚያ መልካም ለሠሩት ሰዎች መልካም ነገርና (ጀነት) ሌላ ተጨማሪም አላቸው። ፊቶቻቸውንም ጥቁረትና ውርደት አይሸፍናቸውም። እነዚያ የገነት ሰዎች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።*

✷ አህመድና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) አንድ ቀን ይህን አንቀፅ አንብበው የሚከተለውን ብለዋል፡- «የጀነት ሰዎች ወደ ጀነት፤ የእሳት ሰዎችም ወደ እሳት ከገቡ በኋላ የጀነት ሰዎች ሆይ! አላህ ያን የቀጠራችሁን ቃል የገባላችሁን ነገር ሊሰጣችሁ ይፈልጋል» የሚል ጥሪ ይተላለፋል። «የጀነት ሰዎችም እሱ ምንድን ነው? የመልካም ስራ ሚዛናችንን አክብዶ፤ ፊታችንን አንፅቶ፤ ጀነት አስገብቶናል ከእሳትም አርቆናል አይደለምን» የለም እንዴ» ይላሉ። ከዚያም በኋላ መጋረጃውን ይገለጥላቸውና ወደ እርሱ ሲመለከቱ እንደ እሱ የሚወዱት እና የሚያስደስታቸው ምንንም ነገር እንዳልሰጣቸው ይምላሉ»

وَٱلَّذِينَ كَسَبُواْ ٱلسَّيِّـَٔاتِ جَزَآءُ سَيِّئَةِۭ بِمِثۡلِهَا وَتَرۡهَقُهُمۡ ذِلَّةٞۖ مَّا لَهُم مِّنَ ٱللَّهِ مِنۡ عَاصِمٖۖ كَأَنَّمَآ
أُغۡشِيَتۡ وُجُوهُهُمۡ قِطَعٗا مِّنَ ٱلَّيۡلِ مُظۡلِمًاۚ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٢٧

27. እነዚያ ኃጢአቶችን የሠሩት ደግሞ ኃጢአቲቱን የሚመጥን ቅጣት አለባቸው። ውርደትም ትሸፍናቸዋለች ለእነርሱ ከአላህ ቅጣት ጠባቂ የላቸውም። ፊቶቻቸው በድቅድቅ ጨለማ ቁራጮች እንደ ተሸፈኑ ይሆናሉ። እነዚያ የእሳት ሰዎች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘለዓለም ነዋሪዎች ናቸው።

وَيَوۡمَ نَحۡشُرُهُمۡ جَمِيعٗا ثُمَّ نَقُولُ لِلَّذِينَ أَشۡرَكُواْ مَكَانَكُمۡ أَنتُمۡ وَشُرَكَآؤُكُمۡۚ فَزَيَّلۡنَا بَيۡنَهُمۡۖ
وَقَالَ شُرَكَآؤُهُم مَّا كُنتُمۡ إِيَّانَا تَعۡبُدُونَ ٢٨ فَكَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدَۢا بَيۡنَنَا وَبَيۡنَكُمۡ إِن كُنَّا
عَنۡ عِبَادَتِكُمۡ لَغَٰفِلِينَ ٢٩ هُنَالِكَ تَبۡلُواْ كُلُّ نَفۡسٖ مَّآ أَسۡلَفَتۡۚ وَرُدُّوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ مَوۡلَىٰهُمُ
ٱلۡحَقِّۖ وَضَلَّ عَنۡهُم مَّا كَانُواْ يَفۡتَرُونَ ٣٠

28-30. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አማልዕክትንና አምላኪዎቻቸውን ሁሉ በአንድ የምንሰበስባቸውንና ከዚያ ለእነዚያ ላጋሩት እናንተም ተጋሪዎቻችሁም ቦታችሁን ያዙ የምንልበትን ተጋሪዎቻቸውም ትገዙ የነበረው እኛን አልነበረም የሚሏቸው ሲሆን በመካከላቸው የምንለይበትን ቀን (አስታውስ)። ጣኦታቶቹ ለእኛ ለመገዛታችሁና ዘንጊዎች ለመሆናችሁ በኛና በእናንተ መካከል የአላህ መስካሪነት በቃ (ይሏቸዋል)። በዚያ ቀን ነፍስ ሁሉ ያሳለፈችውን ሥራ ታውቃለች። (አጋሪዎች) ወደ አላህ እውነተኛ ወደሆነው ጌታቸው ይመለሳሉ። ያ በአላህ ላይ ይቀጣጥፋት የነበሩት ሁሉ ነገርም ይጠፋባቸዋል።

قُلۡ مَن يَرۡزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ أَمَّن يَمۡلِكُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَمَن يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ
ٱلۡمَيِّتِ وَيُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتَ مِنَ ٱلۡحَيِّ وَمَن يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَۚ فَسَيَقُولُونَ ٱللَّهُۚ فَقُلۡ أَفَلَا تَتَّقُونَ ٣١

فَذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمُ ٱلْحَقُّ ۖ فَمَاذَا بَعْدَ ٱلْحَقِّ إِلَّا ٱلضَّلَٰلُ ۖ فَأَنَّىٰ تُصْرَفُونَ ﴿٣٢﴾ كَذَٰلِكَ حَقَّتْ كَلِمَتُ رَبِّكَ عَلَى ٱلَّذِينَ فَسَقُوٓا۟ أَنَّهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿٣٣﴾

**31-33.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማን ነው? መስሚያዎችንና ማያዎችንስ የፈጠረላችሁ ማን ነው? ከሙትም ህያውን የሚያወጣ፤ ከህያውም ሙትን የሚያወጣስ ማን ነው? ነገሩን ሁሉ የሚያስተናብርስ ማን ነው? በላቸው። በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል። ታዲያ (ለምን ታጋራላችሁ?)። ታዲያ አትፈሩትምን? በላቸው። እውነተኛው ጌታችሁ አላህ ብቻ ነው። ከእውነት በኋላ ጥመት እንጂ ሌላ ምን አለ? ከእውነት እንዴት ትዞራላችሁ? ልክ እንደዚሁ የጌታህ ቃል በእነዚያ ባመፁት ሰዎች ላይ ፈፅሞ የማያምኑ መሆናቸው ተረጋገጠ።

قُلْ هَلْ مِن شُرَكَآئِكُم مَّن يَبْدَؤُا۟ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ ۚ قُلِ ٱللَّهُ يَبْدَؤُا۟ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ ۖ فَأَنَّىٰ تُؤْفَكُونَ ﴿٣٤﴾

**34.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከምታጋሯቸው ጣኦታት መካከል መፍጠርን የሚጀምር ከዚያ የሚመልስ አለን? በላቸው። አላህ ግን መፍጠርን ይጀምራል። ከዚያም ይመልሰዋል። ታዲያ ከእምነት እንዴት ትዞራላችሁ? በላቸው።

قُلْ هَلْ مِن شُرَكَآئِكُم مَّن يَهْدِىٓ إِلَى ٱلْحَقِّ ۚ قُلِ ٱللَّهُ يَهْدِى لِلْحَقِّ ۗ أَفَمَن يَهْدِىٓ إِلَى ٱلْحَقِّ أَحَقُّ أَن يُتَّبَعَ أَمَّن لَّا يَهِدِّىٓ إِلَّآ أَن يُهْدَىٰ ۖ فَمَا لَكُمْ كَيْفَ تَحْكُمُونَ ﴿٣٥﴾

**35.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከምታጋሯቸው ጣኦታት መካከልም ወደ እውነት መንገድ የሚመራ አለን? በላቸው። አላህ ግን ወደ እውነቱ ይመራል። ወደ እውነት የሚመራው ጌታ ሊከተሉት የተገባው ነውን? ወይስ ካልተመራ በስተቀር የማይመራው? ለእናንተም ምን አስረጅ አላችሁ? እንዴት በውሸት ትፈርዳላችሁ? በላቸው።

وَمَا يَتَّبِعُ أَكْثَرُهُمْ إِلَّا ظَنًّا ۚ إِنَّ ٱلظَّنَّ لَا يُغْنِى مِنَ ٱلْحَقِّ شَيْـًٔا ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌۢ بِمَا يَفْعَلُونَ ﴿٣٦﴾

**36.** አብዛኞቻቸው ጥርጣሬን እንጂ አይከተሉም። ጥርጣሬ ደግሞ እውነትን በፍፁም አይተካም አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው።

وَمَا كَانَ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانُ أَن يُفۡتَرَىٰ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَلَٰكِن تَصۡدِيقَ ٱلَّذِي بَيۡنَ يَدَيۡهِ
وَتَفۡصِيلَ ٱلۡكِتَٰبِ لَا رَيۡبَ فِيهِ مِن رَّبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٣٧ أَمۡ يَقُولُونَ ٱفۡتَرَىٰهُۖ قُلۡ فَأۡتُواْ بِسُورَةٖ
مِّثۡلِهِۦ وَٱدۡعُواْ مَنِ ٱسۡتَطَعۡتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٣٨ بَلۡ كَذَّبُواْ بِمَا لَمۡ
يُحِيطُواْ بِعِلۡمِهِۦ وَلَمَّا يَأۡتِهِمۡ تَأۡوِيلُهُۥۚ كَذَٰلِكَ كَذَّبَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۖ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ
عَٰقِبَةُ ٱلظَّٰلِمِينَ ٣٩

**37-39.** ይህም ቁርኣን ከአላህ ሌላ ከሆነ ፍጡር የተቀጠፈ ሊሆን አይገባውም። ይልቁንም ያንን ከእርሱ በፊት ያለውን (መጽሐፍ) የሚያረጋግጥና* በመጽሐፉ ውስጥ ያለውን የሚዘረዝር ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእውነት (ሙሐመድ) ቀጣጠፈው ይላሉን? ይህን የሚሉ ከሆነ መሰሉን አንድ ምእራፍ እንኳ እስቲ አምጡ። ለዚህም ጉዳይ ከአላህ ሌላ የቻላችሁትን ሁሉ ረዳት ጥሩ። እውነተኞች እንደሆናችሁ ለዚህ ተጋግዛችሁ አምጡ በላቸው። ይልቁንም ከቁርኣን እውቀቱን ባላዳረሱትና ፍቹም ገና ባልመጣላቸው ነገር አስተባብለዋል። እንደዚሁ እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት አስተባብለዋል። የበዳዮች መጨረሻ እንዴት ይመስል እንደ ነበር በጥሞና ተመልከት።

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድም ነብይ ተዐምራት ሳይሰጡት የተላከ የለም። ሰዎችም በእሱ ዋስትና ሊያገኙ ወይም ሊያምኑ ይችላሉ። ነገር ግን ለእኔ አላህ ወደኔ ያወረደው ራዕይ ነው። ነገ በትንሳኤ ቀን ከእነርሱ በበለጠ እኔ ብዙ ተከታይ ያለኝ እንድሆን እመኛለሁ»

وَمِنۡهُم مَّن يُؤۡمِنُ بِهِۦ وَمِنۡهُم مَّن لَّا يُؤۡمِنُ بِهِۦۚ وَرَبُّكَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُفۡسِدِينَ ٤٠ وَإِن كَذَّبُوكَ
فَقُل لِّي عَمَلِي وَلَكُمۡ عَمَلُكُمۡۖ أَنتُم بَرِيٓـُٔونَ مِمَّآ أَعۡمَلُ وَأَنَا۠ بَرِيٓءٞ مِّمَّا تَعۡمَلُونَ ٤١
وَمِنۡهُم مَّن يَسۡتَمِعُونَ إِلَيۡكَۚ أَفَأَنتَ تُسۡمِعُ ٱلصُّمَّ وَلَوۡ كَانُواْ لَا يَعۡقِلُونَ ٤٢ وَمِنۡهُم مَّن
يَنظُرُ إِلَيۡكَۚ أَفَأَنتَ تَهۡدِي ٱلۡعُمۡيَ وَلَوۡ كَانُواْ لَا يُبۡصِرُونَ ٤٣ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَظۡلِمُ ٱلنَّاسَ شَيۡـٔٗا
وَلَٰكِنَّ ٱلنَّاسَ أَنفُسَهُمۡ يَظۡلِمُونَ ٤٤

**40-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመካከላቸው ወደፊት በቁርኣን የሚያምኑ አሉ። ከእነርሱም መካከል በእርሱ የማያምኑ አሉ። ጌታህ አጥፊዎቹን በጣም ዐዋቂ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢያስተባብሉህም ለእኔ የራሴ ሥራ አለኝ። እናንተም የራሳችሁ ሥራ አላችሁ።

እናንተ እኔ ከምሠራው ተግባር ንፁህ ናችሁ (አትጠየቁም)። እኔም እናንተ ከምትሠሩት ነገር ንፁህ ነኝ (አልጠየቅም በላቸው)። ከእነርሱ መካከል ወደ አንተ ንግግር የሚያዳምጡ የሚሰሙና የማያምኑ አሉ። አንተ ደንቆሮዎችን የማያውቁ ቢሆኑም ታሰማለህን?። ከእነርሱ መካከል ወደ አንተ የሚመለከቱ አሉ። አንተ ልበ እውራንን የማያዩ ቢሆኑም ትመራለህን? አላህ ሰዎችን ምንም አይበድልም። ግን ሰዎች ነፍሶቻቸውን ይበድላሉ።

وَيَوۡمَ يَحۡشُرُهُمۡ كَأَن لَّمۡ يَلۡبَثُوٓاْ إِلَّا سَاعَةٗ مِّنَ ٱلنَّهَارِ يَتَعَارَفُونَ بَيۡنَهُمۡۚ قَدۡ خَسِرَ ٱلَّذِينَ
كَذَّبُواْ بِلِقَآءِ ٱللَّهِ وَمَا كَانُواْ مُهۡتَدِينَ ﴿٤٥﴾ وَإِمَّا نُرِيَنَّكَ بَعۡضَ ٱلَّذِي نَعِدُهُمۡ أَوۡ نَتَوَفَّيَنَّكَ
فَإِلَيۡنَا مَرۡجِعُهُمۡ ثُمَّ ٱللَّهُ شَهِيدٌ عَلَىٰ مَا يَفۡعَلُونَ ﴿٤٦﴾

**45-46.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲዎችን ከቀን አንዲትን ሰዓት እንጂ አንዳልቆዩ መስለው በመካከላቸው የሚተዋወቁ ሲሆኑ በምንሰበስባቸው ቀን የሚከሰተውን (አስታውስ)። እነዚያ በአላህ መገናኘት ያስተባበሉት ሁሉ በእርግጥ ከሰሩ። የተመሩ አልነበሩምና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዚያን የምናስፈራራባቸውን ነገር ውጤት ከፊሉን (በሕይወትህ) ሳለህ ብናሳይህ (መልካም ነው)። ወይም ሳናሳይህ ብንገድልህ ጉዳዩ የእኔ ነው። መመለሻቸው ወደ እኛ ነውና። ከዚያ አላህ በሚሠሩት ሥራ ላይ ሁሉ ዐዋቂ ነው።

وَلِكُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولٞۖ فَإِذَا جَآءَ رَسُولُهُمۡ قُضِيَ بَيۡنَهُم بِٱلۡقِسۡطِ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ ﴿٤٧﴾

**47.** ለህዝቦችም ሁሉ መልዕክተኛ አላቸው። መልዕክተኛው በመጣ ጊዜ በመካከላቸው በትክክል ይፈረዳል። እነርሱም ፍፁም አይበደሉም።

وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلۡوَعۡدُ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٤٨﴾ قُل لَّآ أَمۡلِكُ لِنَفۡسِي ضَرّٗا وَلَا نَفۡعًا إِلَّا
مَا شَآءَ ٱللَّهُۗ لِكُلِّ أُمَّةٍ أَجَلٌۚ إِذَا جَآءَ أَجَلُهُمۡ فَلَا يَسۡتَـٔۡخِرُونَ سَاعَةٗ وَلَا يَسۡتَقۡدِمُونَ ﴿٤٩﴾
قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِنۡ أَتَىٰكُمۡ عَذَابُهُۥ بَيَٰتًا أَوۡ نَهَارٗا مَّاذَا يَسۡتَعۡجِلُ مِنۡهُ ٱلۡمُجۡرِمُونَ ﴿٥٠﴾ أَثُمَّ إِذَا
مَا وَقَعَ ءَامَنتُم بِهِۦٓۚ ءَآلۡـَٰٔنَ وَقَدۡ كُنتُم بِهِۦ تَسۡتَعۡجِلُونَ ﴿٥١﴾ ثُمَّ قِيلَ لِلَّذِينَ ظَلَمُواْ ذُوقُواْ
عَذَابَ ٱلۡخُلۡدِ هَلۡ تُجۡزَوۡنَ إِلَّا بِمَا كُنتُمۡ تَكۡسِبُونَ ﴿٥٢﴾ ۞ وَيَسۡتَنۢبِـُٔونَكَ أَحَقٌّ هُوَۖ قُلۡ إِي
وَرَبِّيٓ إِنَّهُۥ لَحَقّٞۖ وَمَآ أَنتُم بِمُعۡجِزِينَ ﴿٥٣﴾

**48-53.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እውነተኞች ከሆናችሁ የቅጣቱ ቀጠሮ መቼ ነው? ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለራሴ ጉዳትን ማድረስም ሆነ ጥቅምን ማስከበር አላህ ከሻው በስተቀር አልችልም። ለህዝቦች ሁሉ የተወሰነ ጊዜ አላቸው። ጊዜያቸው በደረሰ ወቅት አንዷትን ሰዓት እንኳን አይቆዩም። አይቀደሙምም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እስቲ ንገሩኝ ቅጣቱ በሌሊት ወይም በቀን ቢመጣባችሁ አጋሪዎቹ የሚያስቸኩላቸው ነገር ምንድን ነው? በላቸው። (ከሓዲያን ሆይ!) ከዚያ ቅጣቱ በወደቀ ጊዜ በእርሱ አመናችሁበትን? በእርግጥ በእርሱ የምትቻኮሉ የነበራችሁ ስትሆኑ አሁን ነው የምታውቁትን? (ይባላሉ)። ከዚያ ለእነዚያ ለበደሉት ዘውታሪውን ቅጣት ቅመሱ ትሠሩ የነበራችሁትን እኩይ ተግባር ዋጋ እንጂ አትመነዱም ይባላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱም (ከሞት በኋላ መቀስቀስ እውነት ነውን?) ሲሉ ይጠይቁሃል። አዎን በጌታዬ እምላለሁ እርሱ እውነት ነው። እናንተም አምላጮች አይደላችሁም በላቸው።

وَلَوْ أَنَّ لِكُلِّ نَفْسٍ ظَلَمَتْ مَا فِى ٱلْأَرْضِ لَٱفْتَدَتْ بِهِۦ ۗ وَأَسَرُّوا۟ ٱلنَّدَامَةَ لَمَّا رَأَوُا۟ ٱلْعَذَابَ ۖ وَقُضِىَ بَيْنَهُم بِٱلْقِسْطِ ۚ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿٥٤﴾

**54.** ለበደለችም ነፍስ ሁሉ በምድር ላይ ያለው ሀብት ሁሉ የእርሷ ቢሆን ኖሮ በእርግጥ ቤዛ ባደረገችው ነበር። ቅጣቱንም ባዩ ጊዜ ፀፀትን ይደብቃሉ (ይገልጻሉ)። በመካከላቸውም በትክክል ይፈረዳል። እነርሱ ቅንጣት ያህል አይበደሉም።

أَلَآ إِنَّ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۗ أَلَآ إِنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٥٥﴾ هُوَ يُحْىِۦ وَيُمِيتُ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿٥٦﴾

**55-56.** አስተውሉ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። አስተዉሉ የአላህ የተስፋ ቃል እርግጥ ነው። ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም። እርሱ ሕያው ያደርጋል። ይገድላልም። ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدْ جَآءَتْكُم مَّوْعِظَةٌ مِّن رَّبِّكُمْ وَشِفَآءٌ لِّمَا فِى ٱلصُّدُورِ وَهُدًى وَرَحْمَةٌ لِّلْمُؤْمِنِينَ ﴿٥٧﴾

**57.** (ሰዎች ሆይ!) ከጌታችሁ ዘንድ ግሳጼ በደረቶች ውስጥም ላለው የመጠራጠር በሽታ ፍቱን መድሀኒት፤ ለምዕመናንም ብርሃንና እዝነት የሆነ መልዕክት በእርግጥ መጣላችሁ።

قُلۡ بِفَضۡلِ ٱللَّهِ وَبِرَحۡمَتِهِۦ فَبِذَٰلِكَ فَلۡيَفۡرَحُواْ هُوَ خَيۡرٞ مِّمَّا يَجۡمَعُونَ ٥٨ قُلۡ أَرَءَيۡتُم مَّآ
أَنزَلَ ٱللَّهُ لَكُم مِّن رِّزۡقٖ فَجَعَلۡتُم مِّنۡهُ حَرَامٗا وَحَلَٰلٗا قُلۡ ءَآللَّهُ أَذِنَ لَكُمۡۖ أَمۡ عَلَى ٱللَّهِ
تَفۡتَرُونَ ٥٩ وَمَا ظَنُّ ٱلَّذِينَ يَفۡتَرُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَذُو فَضۡلٍ عَلَى
ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَهُمۡ لَا يَشۡكُرُونَ ٦٠

**58-60.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ችሮታና በእዝነቱ (ይደሰቱ)። በዚህም ምክንያት ይደሰቱ። እርሱ ከሚሰበሰቡት ሀብት ሁሉ በላጭ ነው በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከሲሳይ ለእናንተ ያወረደው ከእርሱም ከፊሉን እርም ከፊሉን የተፈቀደ ያደረጋችሁትን አያችሁን? በላቸው። አላህ ይህንን ለእናንተ ፈቀደላችሁን? ወይስ በአላህ ላይ ትቀጣጥፋላችሁ? በላቸው። እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ ሰዎች በትንሳኤ ቀን በአላህ ጥርጣሬያቸው ምንድን ነው? አይቀጡም ይመስላቸዋልን?አላህ በሰዎች ላይ (ቅጣትን ባለማቻኮል) የልግስና ባለቤት ነው። ግን አብዛኛዎቹ አያመሰግኑትም።

وَمَا تَكُونُ فِي شَأۡنٖ وَمَا تَتۡلُواْ مِنۡهُ مِن قُرۡءَانٖ وَلَا تَعۡمَلُونَ مِنۡ عَمَلٍ إِلَّا كُنَّا عَلَيۡكُمۡ
شُهُودًا إِذۡ تُفِيضُونَ فِيهِۚ وَمَا يَعۡزُبُ عَن رَّبِّكَ مِن مِّثۡقَالِ ذَرَّةٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا فِي ٱلسَّمَآءِ
وَلَآ أَصۡغَرَ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكۡبَرَ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٍ ٦١

**61.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በማንኛውም ነገር ላይ አትሆንም፤ ከእርሱም ከቁርአን ትንሽም አታነብም፤ ማንኛውንም ሥራ አንተም ሆንክ ሰዎቹ አትሠሩም፤ በገባችሁበት ጊዜ በናንተ ተግባር ላይ ተጠባባቂዎች ብንሆን እንጂ በምድርም ሆነ በሰማይ የብናኝ ክብደት ያክል እንኳን ከጌታህ (እውቀት) አይርቅም። ከዚያ ያነሰም ሆነ የተለቀ ነገር የለም በግልፅ መጽሐፍ ውስጥ የተጻፈ ቢሆን እንጂ።

أَلَآ إِنَّ أَوۡلِيَآءَ ٱللَّهِ لَا خَوۡفٌ عَلَيۡهِمۡ وَلَا هُمۡ يَحۡزَنُونَ ٦٢ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَكَانُواْ يَتَّقُونَ ٦٣ لَهُمُ
ٱلۡبُشۡرَىٰ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِۚ لَا تَبۡدِيلَ لِكَلِمَٰتِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ٦٤

**62-64.** አስተውሉ የአላህ ወዳጆች* ከምንም ነገር ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለውም አያዝኑም። እነርሱም እነዚያ ያመኑትና አላህን ሁልጊዜም የሚፈሩት ናቸው። ለእነርሱ በቅርቢቱ ህይወትም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ብስራት አለላቸው። የአላህ ቃል ሁል ጊዜም አይለወጥም። ይህ እርሱ ታላቅ እድል (ስኬታማነት) ነው።

* ወሊይ ማለት ወዳጅ ማለት ሲሆን የአላህ ወልይ ማለት የአላህ ወዳጅ ማለት ነው። ስለዚህ ትክክለኛ የአላህ ወልይ የሚባሉት አዛንን በናፍቆት የሚጠብቁ፤ የሰላትን የመጀመሪያ ተክቢራ እንዳያመልጣቸው የሚዘጋጁ የመጀመሪያውን ሰልፍ ለማግኘት አበክረው መስጊድ የሚገቡ፤ ውስጣቸው ከወንድም ጥላቻ ያፀዱ፤ የሱና ምልክቶች በግልፅ የሚታዩባቸው፤ ዚክር የሚያደርጉ፤ በህላል ላይ ራሱን የገታ፤ አላህ በሰጠው ሀብት የተብቃቃ፤ ቁርአንና ሐዲስን የሚማርና የሚያስተምር፤ ፈገግታ የተላበሰ፤ የሙስሊሞችን ችግር እንደራሱ የሚያይ፤ ልዩነቶችን የማያስፋፉ፤ ፈተናዎችን በትዕግስት የሚወጣ፤ መልካም ነገሮች የሚወድ የሚያበረታታ ሰው ነው።

ቡኻሪ አቡ ሁረይራን ዋቢ አድርገው በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) “ሃያሉ አላህ አሉ የእኔን ወዳጆች የሚተናኮል ሰው እፋለመዋለሁ። ባሪያዬ ግዴታ ያደረግኩበትን ነገር ከመፈጸም የበለጠ ወደ እኔ ሊቃረበው የሚችል ነገር የለም። ባሪያዬ እስከምወደው ድረስ ወደ እኔ ትርፍ የሆኑ ነገሮችን ከመፈፀም አያቋርጥም። ከወደድኩት ደግሞ የሚሰማበት መስሚያ፤ የሚያይበት አይን፤ የሚዳስስበት እጅ የሚሄድበት እግር እሆነዋለሁ። ቢጠይቀኝ እሰጠዋለሁ፤ ጠብቀኝ ካለም እጠብቀዋለሁ» ብለዋል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «የአንድ የሞተ ሰው አስክሬን በሚገባ ተዘጋጅቶ ሰዎች በትከሻቸው ላይ ሲሸከሙት፤ አስክሬኑ የመልካም ሰው አስክሬን ከሆነ«በቶሎ ውሰዱኝ»ይላል። የመጥፎ ሰው አስክሬን ከሆነ ግን «ወይኔ ነፍሴን ወዴት እየወሰዷት ይሆን?» ይላል። ይህን ንግግሩን ከሰው ልጅ በስተቀር በምድር ላይ ያለ ሁሉ ይሰሙታል። የሰው ልጅ ይህን ቢሰማ ኖሮ ራሱን ይስት ነበር»

(ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አላህ መልዕክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፦ «ከብስራቶች በስተቀር በነብይነት ውስጥ ምንም የቀረ የለም» ሶሓቦችም «ብስራቶቹ ምንድን ናቸው?» ብለው ጠየቁ። እሳቸውም «መልካም የሆነ ሕልም ነው» አሉ።

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «የአንድ የፅኑ አማኝ ሰው ሕልም ከአርባ ስድስት የነብይነት ክፍሎች መካከል አንዱ ነው»

وَلَا يَحۡزُنكَ قَوۡلُهُمۡۘ إِنَّ ٱلۡعِزَّةَ لِلَّهِ جَمِيعًاۚ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ٦٥

**65.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ንግግራቸው አያሳዝንህ። ኃይል በሙሉ የአላህ ብቻ ነውና። እርሱ ሰሚና ዐዋቂ ነው።

أَلَآ إِنَّ لِلَّهِ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِۗ وَمَا يَتَّبِعُ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ شُرَكَآءَۚ
إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَإِنۡ هُمۡ إِلَّا يَخۡرُصُونَ ٦٦ هُوَ ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ
لِتَسۡكُنُواْ فِيهِ وَٱلنَّهَارَ مُبۡصِرًاۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَسۡمَعُونَ ٦٧

**66-67.** አስተውሉ። በሰማያትና በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ በእርግጥ የአላህ ብቻ ናቸው። እነዚያ ከአላህ ሌላ ተጋሪዎችን የሚጠሩ ምንን ይከተላሉ? ጥርጣሬን እንጂ ሌላ አይከተሉም። እነርሱ የሚዋሹ ሰዎች እንጂ ሌላ አይደሉም። (ሰዎች ሆይ!) እርሱ ያ ሌሊትን በውስጡ ልታርፉበት ጨለማ ቀንንም ልትሠሩበት ብርሃን ያደረገላችሁ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ህዝቦች ሁሉ በእርግጥ ብዙ ተአምራቶች አሉ።

قَالُواْ ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ وَلَدٗاۗ سُبۡحَٰنَهُۥۖ هُوَ ٱلۡغَنِيُّۖ لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۚ إِنۡ عِندَكُم
مِّن سُلۡطَٰنِۭ بِهَٰذَآۚ أَتَقُولُونَ عَلَى ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٦٨﴾ قُلۡ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَفۡتَرُونَ عَلَى ٱللَّهِ
ٱلۡكَذِبَ لَا يُفۡلِحُونَ ﴿٦٩﴾ مَتَٰعٞ فِي ٱلدُّنۡيَا ثُمَّ إِلَيۡنَا مَرۡجِعُهُمۡ ثُمَّ نُذِيقُهُمُ ٱلۡعَذَابَ ٱلشَّدِيدَ
بِمَا كَانُواْ يَكۡفُرُونَ ﴿٧٠﴾

**68-70.** አላህ ልጅን ያዘ (ወለደ) አሉ። ከሚሉት ሁሉ ጥራት ተገባው። እርሱ በራሱ ተብቃቂ ነው። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። እናንተ ዘንድ በዚህ በምትሉት ምንም አስረጅ የላችሁም። በአላህ ላይ የማታውቁትን ትናገራላችሁን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ ሰዎች ፈጽሞ አይድኑም በላቸው። ለእነርሱ በቅርቢቱ ዓለም ጥቂት ጊዜ ይጠቀሙና ከዚያ መመለሻቸው ወደ እኛ ነው። ከዚያ ይክዱ በነበሩበት ጉዳይ ምክንያት ብርቱን ቅጣት እናቀምሳቸዋለን።

**ከዩኑስ ምዕራፍ ከ (26-70) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ደግን መስራት ምንዳውና ውጤቱ ያማረ፤ መጥፎ ስራ ቅጣቱ አሣማሚ መጨረሻውም የከፋ መሆኑን፤
2. በዱንያ ቆይታቸው በሐሰት ከአላህ ሌላ የሆነን ነገር ሲያመልኩ የነበሩ በሙሉ መልአክ፤ ሰው፤ ዛፍም ይሁን ድንጋይ አምልኩኝ ብሎ ለሰዎች አለማዘዙን በግልፅ ራሱን ነፃ የሚያወጣ መሆኑን፤
3. የቂያማ ዕለት ሰዎች የሰሩትን በሙሉ አንድም ሳይቀር የሚያውቁበት ሁኔታ እንደሚፈጠር፤
4. ቀደምት የአረብ ሙሽሪኮች የአላህን ፈጣሪነት የሚያረጋግጠውን የተውሒድ ክፍል የሚቀበሉ ቢሆንም የአላህን ብቸኛ አምላክነት የሚያረጋግጠውን የተውሒድ ክፍል የሚቃረን ተግባር በማከናወናቸው ሙሽሪኮች ተብለው እንደተፈረጁ፤
5. የአላህ ፈጣሪነትን ማረጋገጥ ብቻ ሙስሊም እንደማያሰኝና ጠቀሜታ እንደሌለው፤
6. እውነት አንድ ብቻ መሆኑና ከእውነት በተቃራኒው ያሉ ነገሮች በሙሉ ውሸት ተብለው የሚጠሩ መሆናቸውን፤
7. በመጥፎ ተግባር ሰምጦ መግባቱ ባለቤቱን እስከሚያጠፋው ድረስ ልምድ እስከመሆን እንደሚደርስ፤

8. የሐሰት አመለካከቶችን በመጀመሪያ መፍጠርም ሆነ ከሞተ በኋላ መመለስ እንደማይችልና እነርሱም እንዳመኑበት ሁሉ ከተቻለም ማስተካከል ግዴታ ስለመሆኑ በማጋለጥ የተውሒድንም ትክክለኛነት ማፅደቅ፤
9. የተሣሣቱ ውሳኔዎችን ኢ. ፍትሐዊ የሆኑ ፍርዶችን መቀበል ተገቢ አለመሆኑን፤
10. እምነት ነክ በሆኑ ነገሮች ላይ በመሰለኝና በነሲብ መጓዝ የማይጠቅም ስለመሆኑና በአጠቃላይ በመሰለኝ መጓዝ ለውድቀትና ለስህተት የሚዳርግ በመሆኑ መጠንቀቅ እንደሚገባ፤
11. የነብዩን (ﷺ) ነብይነትና በእርሳቸው ላይ ይወርዱ የነበሩ ወህዮች ትክክለኛ እንደነበሩ ማረጋገጥ፤
12. ቁርኣን የአላህ ቃል መሆኑን ከሚያስረዱት መካከል ያለፉትን መፅሀፍት ማመኑና ከእርሱ ጋር አለመቃረኑ አንዱ መሆኑን፤
13. የከሓዲያን እንቅስቃሴ በትዕቢትና በክህደት የተሞላ በመሆኑ ምክንያት የአላህን ቅጣት በገሀድ መቅመሳቸውን፤
14. በቁርኣን ትንቢት የተነገረላቸው ድብቅ ነገሮች ሲፈፀሙ በገሀድ መታየቱ፤
15. ነብዩ (ﷺ) ከከሓዲያን ጋር በምን አይነት መልኩ መከራከር እንዳለባቸው፤
16. አላህ ማንንም ሰው ቅንጣት ያህል የማይበድል መሆኑንና ሰዎች ግን ራሳቸውን በራሳቸው የሚበድሉ መሆናቸውን፤
17. ነብዩ ሙሐሙድ (ﷺ) ከአላህ ወህይ የወረደላቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤
18. ነገሮችን ዕርም ማድረግ እና ነገሮችን መፍቀድ ከአላህ ብቸኛ ስልጣኖቹ አንዱ ስለመሆኑ፤
19. በአላህ ላይ መዋሸት ከፍተኛ ወንጀል ስለመሆኑ፤
20. አላህ ለሰዎች ታላላቅ ውለታዎችን የዋለ ቢሆንም ብዙ ሰዎች ይህንን ፀጋ በማሰብ ለአላህ ምስጋና የማያደርሱ መሆኑን፤
21. የአላህን ድንጋጌዎች ዘወትር በማሰብ እርሱን መጠባበቅና የምእመናን መለያ መሆኑ፤
22. ለውሐል ማህፉዝ ተብሎ የሚጠራ ሰሌዳ መኖሩን፤
23. ምግብ የተባለን ሁሉ መመገብ በሸሪዐ ካልተከለከለ በስተቀር የተፈቀደ እንደሆነ፤
24. አላህን በመታዘዝ የእርሱን ወዳጅነት ማግኘት እንደሚቻልና የአላህ ወዳጆች የሚባሉት አማኞች መሆናቸውን፤
25. የአላህ ፍራቻ ያደረባቸው ባሪያዎቹ ብቻ እንደሆኑ፤
26. የአላህ ንግግር እውነተኛና ትክክለኛ ፍርዱም ፍትሃዊና የማይሻር ስለመሆኑ፤
27. አስተማሪ የሆነ ሰው የሐሰተኞች ፕሮፖጋንዳ ሊበግረውና ሊያሣዝነው እንደማይገባ፤
28. እንዲሁም በሐሰተኞች አሉባልታ በመደናገጥ ከማስተማር ስራው መገታት እንደሌለበት፤
29. ክብር የአላህ ብቻ መሆኑን፤
30. ከአላህ ሌላ የሆኑ የሐሰት አማልክት ቅንጣት ታህል እንኳን ለአምላክነታቸው ማስረጃ የሌላቸው መሆኑን፤
31. አላህ በመፍጠርና በማስተናበርና የተብቃቃ ኃያል ጌታ መሆኑ ለብቸኛ አምላክነቱ በቂ ማስረጃ ስለ መሆኑ፤
32. ማንኛውም ጉድለትን የሚያንፀባርቅ ባህርይ ለአላህ መስጠትና ለእርሱ ሌላን ማስጠጋት የተከለከለ ስለመሆኑ፤
33. በማስረጃ ላይ ያልተመሠረቱ ክርክሮች በሙሉ ውጤት የሌላቸውና ውድቅ መሆናቸውን፤

34. ጠንቋዮች፣ የቢድዐና የግል ስሜት አራማጅ ች በሙሉ የሐሰት አራማጆች በመሆናቸው መጨረሻቸው ኪሣራ መሆኑን፤
35. አማኝ የሆነ ሰው ሐሰተኞች የሚያገኟቸውን ጊዜያዊና አላፊ ብልጭልጮች ሊቀና ሊሸነገል እንደማይገባ እንማራለን።

۞ وَٱتۡلُ عَلَيۡهِمۡ نَبَأَ نُوحٍ إِذۡ قَالَ لِقَوۡمِهِۦ يَٰقَوۡمِ إِن كَانَ كَبُرَ عَلَيۡكُم مَّقَامِي وَتَذۡكِيرِي
بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ فَعَلَى ٱللَّهِ تَوَكَّلۡتُ فَأَجۡمِعُوٓاْ أَمۡرَكُمۡ وَشُرَكَآءَكُمۡ ثُمَّ لَا يَكُنۡ أَمۡرُكُمۡ عَلَيۡكُمۡ
غُمَّةً ثُمَّ ٱقۡضُوٓاْ إِلَيَّ وَلَا تُنظِرُونِ ﴿٧١﴾ فَإِن تَوَلَّيۡتُمۡ فَمَا سَأَلۡتُكُم مِّنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا
عَلَى ٱللَّهِۖ وَأُمِرۡتُ أَنۡ أَكُونَ مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ﴿٧٢﴾ فَكَذَّبُوهُ فَنَجَّيۡنَٰهُ وَمَن مَّعَهُۥ فِي ٱلۡفُلۡكِ
وَجَعَلۡنَٰهُمۡ خَلَٰٓئِفَ وَأَغۡرَقۡنَا ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَاۖ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُنذَرِينَ ﴿٧٣﴾
ثُمَّ بَعَثۡنَا مِنۢ بَعۡدِهِۦ رُسُلًا إِلَىٰ قَوۡمِهِمۡ فَجَآءُوهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَمَا كَانُواْ لِيُؤۡمِنُواْ بِمَا كَذَّبُواْ
بِهِۦ مِن قَبۡلُۚ كَذَٰلِكَ نَطۡبَعُ عَلَىٰ قُلُوبِ ٱلۡمُعۡتَدِينَ ﴿٧٤﴾

**71-74.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የኑህን ወሬ በእነርሱ ላይ አንብብላቸው። ለህዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውሱ) ህዝቦቼ ሆይ! በእናንተ ውስጥ ብዙን ጊዜ መቆየቴ የአላህን ተዐምራት ለእናንተ ማስታወሴ በእናንተ ላይ የከበደ ቢሆንም በአላህ ላይ ተጠግቻለሁ። ነገራችሁንም ከምታጋሯቸው ጣኦታት ጋር ሆናችሁ እስቲ ቁረጡ። ከዚያ ነገራችሁ በእናንተ ላይ ድብቅ አይሁን (ግለፁት)። ከዚያ የሻችሁትን ወደ እኔ አድርሱ። ጊዜም አትስጡኝ (ከምንም አይቆጥራችሁም)። ብትሸሹም አትጎዱኝም። ከምንዳ ምንንም አልለምናችሁምና ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም። ከሙስሊሞች እንድሆንም ታዝዣለሁ። አስተባበሉት እርሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች በታንኳይቱ ውስጥ አዳንናቸው። ለጠፉት ምትኮች አደረግናቸው። እነዚያንም በአንቀፆቻችን ያስተባበሉትን አሰመጥን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የተስፈራሩት ህዝቦች መጨረሻ እንዴት እንደ ነበር እስቲ ተመልከት። ከዚያ ከእርሱ በኋላ መልዕክተኞችን ወደየ ህዝቦቻቸው ላክን። በግልጽ ማስረጃዎችም መጧቸው። ከመላካቸው በፊት በእርሱ ባስተባበሉት ነገር የሚያምኑ አልሆኑም። ልክ እንደዚሁ በወሰን አላፊዎች ልቦች ላይ እናትማለን።

ثُمَّ بَعَثۡنَا مِنۢ بَعۡدِهِم مُّوسَىٰ وَهَٰرُونَ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ وَمَلَإِيْهِۦ بِـَٔايَٰتِنَا فَٱسۡتَكۡبَرُواْ وَكَانُواْ قَوۡمٗا
مُّجۡرِمِينَ ﴿٧٥﴾ فَلَمَّا جَآءَهُمُ ٱلۡحَقُّ مِنۡ عِندِنَا قَالُوٓاْ إِنَّ هَٰذَا لَسِحۡرٞ مُّبِينٞ ﴿٧٦﴾ قَالَ مُوسَىٰٓ
أَتَقُولُونَ لِلۡحَقِّ لَمَّا جَآءَكُمۡۖ أَسِحۡرٌ هَٰذَا وَلَا يُفۡلِحُ ٱلسَّٰحِرُونَ ﴿٧٧﴾ قَالُوٓاْ أَجِئۡتَنَا لِتَلۡفِتَنَا
عَمَّا وَجَدۡنَا عَلَيۡهِ ءَابَآءَنَا وَتَكُونَ لَكُمَا ٱلۡكِبۡرِيَآءُ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا نَحۡنُ لَكُمَا بِمُؤۡمِنِينَ ﴿٧٨﴾
وَقَالَ فِرۡعَوۡنُ ٱئۡتُونِي بِكُلِّ سَٰحِرٍ عَلِيمٖ ﴿٧٩﴾ فَلَمَّا جَآءَ ٱلسَّحَرَةُ قَالَ لَهُم مُّوسَىٰٓ أَلۡقُواْ مَآ أَنتُم
مُّلۡقُونَ ﴿٨٠﴾ فَلَمَّآ أَلۡقَوۡاْ قَالَ مُوسَىٰ مَا جِئۡتُم بِهِ ٱلسِّحۡرُۖ إِنَّ ٱللَّهَ سَيُبۡطِلُهُۥٓ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُصۡلِحُ
عَمَلَ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ﴿٨١﴾ وَيُحِقُّ ٱللَّهُ ٱلۡحَقَّ بِكَلِمَٰتِهِۦ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡمُجۡرِمُونَ ﴿٨٢﴾

**75-82.** ከዚያ ከእነርሱ በኋላ ሙሳንና ሃሩንን ወደ ፈርኦንና ወደ መማክርቱ በተአምራታችን ላክን። ኮሩም። ትእቢተኞች ህዝቦችም ነበሩ። ከእኛም ዘንድ እውነቱ በመጣላቸው ጊዜ ይህ በእርግጥ ግልጽ ድግምት ነው አሉ። ሙሳ፡- እውነቱን በመጣላችሁ ጊዜ ድግምተኞች የማይድኑ ሲሆኑ እርሱ ድግምት ነው ትላላችሁን? ይህ ድግምት ነውን? አለ። እነርሱም አባቶቻችንን ካገኘንበት ሃይማኖት ልታዞሩንና በምድር ውስጥ ለእናንተም ኩራት ሹመት ልትኖራችሁ መጣህብን። እኛ ለእናንተ በፍፁም አማኞች አይደለንም አሉ። ፈርኦን፡- ዐዋቂ ድግምተኛን ሁሉ አምጡልኝ አለ። ድግምተኞቹ በመጡ ጊዜም ሙሳ ለእነርሱ፡- እናንተ የምትጥሉትን ነገር ጣሉ አላቸው። ገመዶቻቸውን በጣሉም ጊዜ ሙሳ፡- ያ በእርሱ የመጣችሁበት ነገር ድግምት ነው። አላህ በእርግጥ ያፈርሰዋል። አላህ የአጥፊዎችን ሥራ ፈጽሞ አያበጅምና አለ። አላህም ከሓዲያን ቢጠሉም እውነትን በቃላቱ ያረጋግጣል።

فَمَآ ءَامَنَ لِمُوسَىٰٓ إِلَّا ذُرِّيَّةٞ مِّن قَوۡمِهِۦ عَلَىٰ خَوۡفٖ مِّن فِرۡعَوۡنَ وَمَلَإِيْهِمۡ أَن يَفۡتِنَهُمۡۚ وَإِنَّ
فِرۡعَوۡنَ لَعَالٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَإِنَّهُۥ لَمِنَ ٱلۡمُسۡرِفِينَ ﴿٨٣﴾ وَقَالَ مُوسَىٰ يَٰقَوۡمِ إِن كُنتُمۡ ءَامَنتُم
بِٱللَّهِ فَعَلَيۡهِ تَوَكَّلُوٓاْ إِن كُنتُم مُّسۡلِمِينَ ﴿٨٤﴾ فَقَالُواْ عَلَى ٱللَّهِ تَوَكَّلۡنَا رَبَّنَا لَا تَجۡعَلۡنَا فِتۡنَةٗ لِّلۡقَوۡمِ
ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٨٥﴾ وَنَجِّنَا بِرَحۡمَتِكَ مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿٨٦﴾ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰ وَأَخِيهِ أَن
تَبَوَّءَا لِقَوۡمِكُمَا بِمِصۡرَ بُيُوتٗا وَٱجۡعَلُواْ بُيُوتَكُمۡ قِبۡلَةٗ وَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَۗ وَبَشِّرِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٨٧﴾
وَقَالَ مُوسَىٰ رَبَّنَآ إِنَّكَ ءَاتَيۡتَ فِرۡعَوۡنَ وَمَلَأَهُۥ زِينَةٗ وَأَمۡوَٰلٗا فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا رَبَّنَا لِيُضِلُّواْ
عَن سَبِيلِكَۖ رَبَّنَا ٱطۡمِسۡ عَلَىٰٓ أَمۡوَٰلِهِمۡ وَٱشۡدُدۡ عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ فَلَا يُؤۡمِنُواْ حَتَّىٰ يَرَوُاْ ٱلۡعَذَابَ
ٱلۡأَلِيمَ ﴿٨٨﴾ قَالَ قَدۡ أُجِيبَت دَّعۡوَتُكُمَا فَٱسۡتَقِيمَا وَلَا تَتَّبِعَآنِّ سَبِيلَ ٱلَّذِينَ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٨٩﴾

**83-89.** ለሙሳም ከፊርአንና ከሹማምንቶቻቸው ማሰቃየትን ከመፍራት ጋር ከወገኖቹ*[1] ጥቂት ትውልዶች ብቻ እንጂ አላመኑለትም። ፊርአንም በምድር ላይ በእርግጥ ይኮራ ነበር እርሱም በእርግጥ ወሰን ካለፉት ነበር። ሙሳም፡- ህዝቦቼ ሆይ! በአላህ አምናችሁ እንደ ሆነ በእርሱ ላይ ብቻ ተጠጉ። ታዛዥች እንደ ሆናችሁ (በአላህ ላይ ብቻ ትመካላችሁ) አለ። አሉ፡- በአላህ ላይ ተጠጋን። ጌታችን ሆይ! ለበደለኞች ህዝቦች መፈተኛ አታድርገን። በእዝነትህም ከከሓዲዎች ህዝቦች ግፍ አድነን። ወደ ሙሳና ወደ ወንድሙ፡ ለህዝቦቻችሁ በግብፅ ውስጥ ቤቶችን ሥሩ። ቤቶቻችሁንም መስገጃ*[2] አድርጉ። ሶላትንም በደንቡ ስገዱ። (ለሙሳ) ምዕመናኖቹንም አብስር ስንል ላክን። ሙሳም፣ ጌታችን ሆይ! አንተ ለፊርአንና ለሹሞች በቅርቢቱ ህይወት ጌጥን ብዙ ገንዘቦችንም በእርግጥ ሰጠህ። ጌታችን ሆይ! ከመንገድህ ያሳስቱ ዘንድ ሰጠሃቸው። ጌታችን ሆይ! ገንዘቦቻቸውን አጥፋ። በልቦቻቸውም ላይ አትም። አሳማሚን ቅጣት አስከሚያዩ አያምኑምና። አላህ፡- ፀሎታችሁ ተሰምታለች። ቀጥም በሉ። የእነዚያን የማያውቁትን ሰዎች መንገድ አትከተሉ አላቸው።

*1 ይህ አባባል ከራሱ ከፊርዖን ቤተሰቦች ማለት ሊሆን እንደሚችልም ነው። ምክንያቱም የፊርዖን ባለቤት፣ አንድ ሰውዬ፣ የልጁ ፀጉር ቤት፣ የካዝና ሃላፊው ሚስት በትክክለኛው እምነት አምነው ነበርና ነው።

*2 የቤቶቻችሁን ፊት ወደ ቂብላችሁ በይተል መቅዲስ አዙሩት ወይም ቤቶቻችሁን ፊት ለፊት አድርጉ ማለት ነውም ተብሏል።

**ከዩኑስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (71-87) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የነብዩን (ﷺ) ታሪክ በማውሳት አስተማሪዎችን የሚያፅናና ቁርአናዊ ተስተምህሮ፣
2. ተወኩል መልካም ውጤትና ያማረ ፍሬ እንዳለው፣
3. ለአላህ ተብሎ የሚሰጥን ኢስላማዊ ትምህርት የሚያስተምር ሰው ችግሩ ከአቅሙ በላይ ካልሆነበት በስተቀር በሚያስተምረው ትምህርት ደመወዝ መቀበል እንደማይገባ፣
4. የአስተባባዮች መጨረሻ አሣማሚ ቅጣትና ውርደትን መከናነብ ስለ መሆኑ፣
5. መጥፎ ነገሮችን መቅረብ የተከለከለ ከመሆኑ ጋር በመጥፎ ነገሮች ጠልቆ መግባቱ ደግሞ ለግለሰቡ አደገኛ ውጤት ስለሚያመጣ በጥብቅ የተወገዘ መሆኑን፣
6. ኩራት በራሱ የተወገዘ ብልሹ ምግባር ከመሆኑም በላይ ለብዙ ወንጀሎች ዋና ምክንያት የሚሆን አስቀያሚ ባህሪ መሆኑን፣
7. ድግምተኛነት መቼውም ቢሆን ከአላህ ቅጣት ነፃ የማያወጣ ስለ መሆኑ፣
8. የሐሰት ወሬን መንዛት፣ ያልተረጋገጡና በጥርጣሬ ላይ የተመሰረቱ ነገሮችን ማስወራት የሐሰተኞች ባህሪይ ስለ መሆኑ፣
9. ድግምት በብዙ አይነት መንገዶች ሊታወቅ የሚችልና የካበተ እውቀት ያላቸው ደጋሚዎች ያሉበት ቢሆንም ወንጀል መሆኑን፣
10. ድግምትን መማሩም ሆነ ድግምትን መጠቀሙ ክልክል ስለ መሆኑ፣

11. ድግምተኛ የሆነ ሰው ምድራዊ ቅጣቱ የሞት ፍርድ እንደሆነ፤
12. እውነትን ለማንገስና ለመደገፍ ሐሰትን ለማንኳሰስና ለመቃወም ከጠላት ጋር መፎካከርና መውራረድ የተፈቀደ መሆኑን፤
13. ከውሸት ጋር በሚያደርገው ትግል ምንግዜም ሐቅ አሸናፊ፤ ውሸት ተሸናፊ እንደሚሆን፤
14. ነብዩ ሙሣ ነብያዊ ተልዕኳቸውን በድል ማጠናቀቃቸውን በማውሣት ነብዩም (ﷺ) በፅናት እንዲቆሙ የሚያስተምር የማፅናኛ ቁርአናዊ ተስተምህሮዎች፤
15. ኩራትና ማባከን የተከለከሉ ጉዳዮች በመሆናቸው ኩራተኞችና አባካኞች የተወገዙ ስለመሆናቸው፤
16. የዳዕዋን ኃላፊነትና በአላህ ላይ መመካት ያለው ሚና ከፍተኛ ስለ መሆኑ፤
17. ፀሎት እጅግ ተፈላጊ የዒባዳ ዘርፍ መሆኑንና ወደ አላህ ለመቃረብ በመልካም ስሞቹና በጥሩ ባህሪያቶቹ እርሱን መለመን ተገቢ መሆኑን፤
18. በሕይወቱና ንብረት ላይ አደጋ የሚያደርስ ነገር መኖሩን የሰጋ ሰው በየቤቱ መስገድ የሚችል መሆኑ፤
19. ምእመናንና ለትክክለኛ ሠጋጆች መጨረሻቸው ያማረ እንደሚሆን ቁርአናዊ ብስራት፤
20. ሶላትን መስገድ ግዴታ ስለመሆኑ እንማራለን።

۞ وَجَٰوَزْنَا بِبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ ٱلْبَحْرَ فَأَتْبَعَهُمْ فِرْعَوْنُ وَجُنُودُهُۥ بَغْيًا وَعَدْوًا ۖ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَدْرَكَهُ ٱلْغَرَقُ قَالَ ءَامَنتُ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱلَّذِىٓ ءَامَنَتْ بِهِۦ بَنُوٓا۟ إِسْرَٰٓءِيلَ وَأَنَا۠ مِنَ ٱلْمُسْلِمِينَ ﴿٩٠﴾ ءَآلْـَٰٔنَ وَقَدْ عَصَيْتَ قَبْلُ وَكُنتَ مِنَ ٱلْمُفْسِدِينَ ﴿٩١﴾ فَٱلْيَوْمَ نُنَجِّيكَ بِبَدَنِكَ لِتَكُونَ لِمَنْ خَلْفَكَ ءَايَةً ۚ وَإِنَّ كَثِيرًا مِّنَ ٱلنَّاسِ عَنْ ءَايَٰتِنَا لَغَٰفِلُونَ ﴿٩٢﴾

**90-92.** የኢስራኤል ልጆችን ባህሩን አሳለፍናቸው። ፈርኦንና ሰራዊቱም ወሰን ለማለፍና ለመበደል ተከተሏቸው። የመስመጥ አደጋ ባገኘው ጊዜ አመንኩ። እነሆ ከዚያ የእሥራኤል ልጆች ከአመኑበት አምላክ በስተቀር ሌላ የእውነት አምላክ የለም። እኔም ከታዛዦቹ አንዱ ነኝ አለ። ከአሁን በፊት በእርግጥ ያመፅክና ከአጥፊዎችም የነበርክ ስትሆን አሁን ታምናለህን? ተባለ። እናም ዛሬ ከኋላህ ለሚመጡ ትውልዶች ተዐምር ትሆን ዘንድ አካልህን (ከባሕሩ) እናወጣሀለን ከሰዎችም ብዙዎቹ ከተዐምሮቻችን በእርግጥ ዘንጊዎች ናቸው።

وَلَقَدْ بَوَّأْنَا بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ مُبَوَّأَ صِدْقٍ وَرَزَقْنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ فَمَا ٱخْتَلَفُوا۟ حَتَّىٰ جَآءَهُمُ ٱلْعِلْمُ ۚ إِنَّ رَبَّكَ يَقْضِى بَيْنَهُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ فِيمَا كَانُوا۟ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ﴿٩٣﴾

**93.** የኢስራኤልን ልጆችም ምስጉንን ስፍራ በእርግጥ አሰፈርናቸው። ከመልካም ሲሳዮችም ሰጠናቸው። እውቀትም እስከመጣላቸው ድረስ አልተለያዩም። ጌታህ በእርሱ ይለያዩበት በነበሩት ነገር በትንሳኤ ቀን በመካከላቸው ይፈርዳል።

فَإِن كُنتَ فِي شَكٍّ مِّمَّآ أَنزَلْنَآ إِلَيْكَ فَسْـَٔلِ ٱلَّذِينَ يَقْرَءُونَ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلِكَ ۚ لَقَدْ جَآءَكَ
ٱلْحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُمْتَرِينَ ﴿٩٤﴾ وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ
فَتَكُونَ مِنَ ٱلْخَٰسِرِينَ ﴿٩٥﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ حَقَّتْ عَلَيْهِمْ كَلِمَتُ رَبِّكَ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿٩٦﴾
وَلَوْ جَآءَتْهُمْ كُلُّ ءَايَةٍ حَتَّىٰ يَرَوُا۟ ٱلْعَذَابَ ٱلْأَلِيمَ ﴿٩٧﴾

**94-97.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ አንተ ካወረድነው በመጠራጠር ውስጥ ከሆንክ እነዚያን ከአንተ በፊት መጽሐፉን የሚያነቡትን ሰዎች ጠይቅ። እውነቱ ከጌታህ ዘንድ በእርግጥ መጥቶልሃል። እናም ከተጠራጣሪዎች አትሁን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነዚያ የአላህን አንቀፆች ካስተባበሉት ሰዎች አትሁን። ከከሳሪዎቹ ትሆናለህና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በእነርሱ ላይ የጌታህ ቃል የተረጋገጠባቸው ተአምራት ሁሉ ቢመጣላቸውም አሳማሚን ቅጣት እስከሚያዩ ድረስ አያምኑም።

**ከዩኑስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (88-97) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ግፈኛ ሁሉ ከምድር ላይ እንዲጠፋ ፀሎት (ዱዓ) የማድረግን ተገቢነት፤
2. የገንዘብ መብዛትና የሀብት መጥለቅለቅ እንዲሁም ለምድራዊ አላቂ ሕይወትና ብልጭልጭ ነገሮች መታለል ለጥፋት የሚጋብዝ ስለመሆኑ፤
3. እጅግ በተሳሳተ የጥመት መንገድ ላይ በጥልቅ የገቡ ሰዎች የመጨረሻው ሕይወታቸው ለክህደት የተጋለጠ በመሆኑ በክህደት ውስጥ ሆነው የመሞት እድላቸው ሰፊ እንደሆነ፤
4. በፀሎት ወቅት «አሜን» ሲል ፀሎት አድራጊውን የተቀበለ ሰው ለራሱ ፀሎት እንዳደረገ የሚቆጠር መሆኑን፤
5. የተሣሣቱ የመሐይማንን ጎዳና መከተል ተገቢ አለመሆኑን፤
6. ከማንኛውም ሐይማኖትና አመለካከት የበለጠውና የተሻለው ሃይማኖት ኢስላም መሆኑን፤
7. አብዛኛው የሰው ልጆች ነገ ምን ሊሆኑ እንደሚችሉ የማያውቁና ችግሮች መጥተው እስከሚደርሱባቸው ድረስ ዝንጉ መሆናቸውን፤
8. ሙስሊሞች የተሰጣቸው ክብርና ማዕረግ ከፍ ያለ መሆኑን፤
9. መልካም ተብሎ የሚጠራው ምግብና መጠቀሚያ በሀላል መንገድ የተገኘው ብቻ ስለ መሆኑ፤
10. አላህ ሊያጠፋቸው የሚያስባቸውን ህዝቦች እርስ በርሳቸው እንደሚያቃቅራቸውና የሚከፋፍላቸው ስለመሆኑ፤
11. በእምነት ጉዳዮች ላይ መከፋፈልና የተለያዩ ህግ ወጥ አቋሞችን መያዝ የተከለከ ስለመሆኑ፤
12. የቂያማ ዕለት የተከፋፈሉ ሰዎችን በተመለከተ የማያዳግም ውሳኔ የሚሰጥ ስለ መሆኑ፤
13. የነብዩ (ﷺ) ትክክለኛ ነብይነት የተረጋገጠ መሆኑን ማረጋገጥ፤
14. የማያውቅ ሰው በማንኛውም ርዕስ ጉዳይ ላይ አዋቂዎችን እየጠየቀ መማር የሚገባው መሆኑን፤
15. የአላህን ቁርአናዊ አናቅፅ ማስተባበል ክህደት መሆኑን፤
16. መሰረታዊ በሆኑ ኢስላማዊ ድንጋጌዎች ላይ ጥርጣሬና ቅጥፈት ኢስላምን ማስተባበልና ክህደት ስለመሆኑ፤
17. በቀዷና ቀደር ማመን ከመሰረታዊ የኢስላም እውነታዎች አንዱ መሆኑን እንማራለን።

فَلَوۡلَا كَانَتۡ قَرۡيَةٌ ءَامَنَتۡ فَنَفَعَهَآ إِيمَٰنُهَآ إِلَّا قَوۡمَ يُونُسَ لَمَّآ ءَامَنُواْ كَشَفۡنَا عَنۡهُمۡ عَذَابَ
ٱلۡخِزۡيِ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَمَتَّعۡنَٰهُمۡ إِلَىٰ حِينٖ ﴿٩٨﴾

**98.** ከነብዩ ዩኑስ በፊት ካለፉት ከተሞች ያመነችና እምነቷ የጠቀማት ከተማ ለምን አልኖረችም? ግን የነብዩ ዩኑስ ህዝቦች ባመኑ ጊዜ በቅርቢቱ ህይወት የውርደትን ቅጣት ከእነርሱ ላይ አነሳንላቸው። እስከ ጊዜም ድረስ አጣቀምናቸው።

وَلَوۡ شَآءَ رَبُّكَ لَأٓمَنَ مَن فِي ٱلۡأَرۡضِ كُلُّهُمۡ جَمِيعًاۚ أَفَأَنتَ تُكۡرِهُ ٱلنَّاسَ حَتَّىٰ يَكُونُواْ مُؤۡمِنِينَ ﴿٩٩﴾
وَمَا كَانَ لِنَفۡسٍ أَن تُؤۡمِنَ إِلَّا بِإِذۡنِ ٱللَّهِۚ وَيَجۡعَلُ ٱلرِّجۡسَ عَلَى ٱلَّذِينَ لَا يَعۡقِلُونَ ﴿١٠٠﴾

**99-100.** ጌታህም በሻ ኖሮ በምድር ያሉት ሰዎች ሁሉ በአንድ የተሰበሰቡ ሆነው ባመኑ ነበር። ታዲያ አንተ ሰዎችን አማኞች እንዲሆኑ ታስገድዳለህን? ማንኛዋም ነፍስ በአላህ ፈቃድ* ቢሆን እንጂ ልታምን አትችልም። አላህ ለከፊሎቹ እምነትን ይሻል በእነዚያ በማያውቁት ላይ ርክሰትን ያደርጋል።

* ይህ አንቀፅ ከብዙ ተመሳሳይ አናቅፅ ጋራ ሲገናዘብ ማለትም «አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም....» (28/56) «በመቅናታቸው ላይ ብትጓጓ ምንም ልታደርግ...» (16/37) «በርሱ ላይ የቅጣት ቃል የተረጋገጠችበት ሰው...» (39/19) «መጥፎ ስራው የተሸለመለትና መልካም አድርጎ ያየው....» (35/8)

በሌላ አንቀጽ አንተ ወደ ትክክለኛው መንገድ ትመራለህ ከሚለው ጋር ስናስማማው የመጀመሪያዎች አንቀጾች (ሂዳየት አት ተውፊቅ) ልብን ወደ ትክክለኛው መንገድ የመምራት መብት የአላህ ብቻ ነው 2ኛው ሂደየት (አል ኢርሻድ) ይባላል ትክክለኛውን መንገድ ማመላከት ለነቢዩ (ﷺ) መሆኑን ይጠቅሳል።

قُلِ ٱنظُرُواْ مَاذَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَا تُغۡنِي ٱلۡأٓيَٰتُ وَٱلنُّذُرُ عَن قَوۡمٖ لَّا يُؤۡمِنُونَ ﴿١٠١﴾
فَهَلۡ يَنتَظِرُونَ إِلَّا مِثۡلَ أَيَّامِ ٱلَّذِينَ خَلَوۡاْ مِن قَبۡلِهِمۡۚ قُلۡ فَٱنتَظِرُوٓاْ إِنِّي مَعَكُم مِّنَ
ٱلۡمُنتَظِرِينَ ﴿١٠٢﴾ ثُمَّ نُنَجِّي رُسُلَنَا وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْۚ كَذَٰلِكَ حَقًّا عَلَيۡنَا نُنجِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿١٠٣﴾

**101-103.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሰማያትና በምድር ውስጥ ያሉትን ተዐምራት ተመልከቱ በላቸው። ሆኖም ተዐምራቶችና አስፈራሪዎች ለማያምኑ ህዝቦች ምንም አይጠቅሙም። የእነዚያን ከእነርሱ በፊት ያለፉትን ህዝቦች ቀኖች ብጤ ያገኟቸውን አይነት ቀናትን እንጂ ሌላን ይጠባበቃሉን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተም ተጠባበቁ እኔም ከናንተው ጋር ከሚጠባበቁት ነኝ በላቸው። ከዚያም መልዕክተኞቻችንንና እነዚያን ያመኑትንም ከጭንቅ ሁሉ እናድናለን። ልክ እንደዚሁ አማኞችን (ከጭንቅ ሁሉ) ማዳን በእኛ ላይ ተረጋገጠ።

قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِن كُنتُمۡ فِي شَكّٖ مِّن دِينِي فَلَآ أَعۡبُدُ ٱلَّذِينَ تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ
وَلَٰكِنۡ أَعۡبُدُ ٱللَّهَ ٱلَّذِي يَتَوَفَّىٰكُمۡۖ وَأُمِرۡتُ أَنۡ أَكُونَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١٠٤

**104.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎች ሆይ! ከእኔ ሃይማኖት በመጠራጠር ውስጥ ከሆናችሁ እነዚያን ከአላህ ሌላ የምትገዟቸውን አልገዛም። ይልቁንም ያንን የሚገድላችሁን አላህን እገዛለሁ። ከትክክለኛ አማኞች እንድሆንም ታዝዣለሁ በላቸው።

وَأَنۡ أَقِمۡ وَجۡهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفٗا وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡمُشۡرِكِينَ ١٠٥ وَلَا تَدۡعُ مِن دُونِ ٱللَّهِ
مَا لَا يَنفَعُكَ وَلَا يَضُرُّكَۖ فَإِن فَعَلۡتَ فَإِنَّكَ إِذٗا مِّنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ١٠٦ وَإِن يَمۡسَسۡكَ ٱللَّهُ بِضُرّٖ
فَلَا كَاشِفَ لَهُۥٓ إِلَّا هُوَۖ وَإِن يُرِدۡكَ بِخَيۡرٖ فَلَا رَآدَّ لِفَضۡلِهِۦۚ يُصِيبُ بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦۚ
وَهُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ١٠٧

**105-107.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ፊትህን ወደ ቀጥታው መንገድ ያዘነበልክ ስትሆን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ። ከአጋሪዎቹም አትሁን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአላህ በስተቀር የማይጠቅምንና የማይጎዳን አትገዛ። ይህን ብትሠራ ግን ያን ጊዜ ከበደለኞቹ ትሆናለህ (ተብያለሁ በላቸው)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ጉዳትን ቢያደርስብህ ከእርሱ ሌላ ለእርሱ ገላጭ የለውም። በጎን ነገርም ቢሻልህ ለችሮታው መላሽ ማንም የለም። ከባሮቹ የሚሻውን በእርሱ ይለይበታል። እርሱም መሓሪና አዛኝ ነው።

قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ قَدۡ جَآءَكُمُ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكُمۡۖ فَمَنِ ٱهۡتَدَىٰ فَإِنَّمَا يَهۡتَدِي لِنَفۡسِهِۦۖ
وَمَن ضَلَّ فَإِنَّمَا يَضِلُّ عَلَيۡهَاۖ وَمَآ أَنَا۠ عَلَيۡكُم بِوَكِيلٖ ١٠٨

**108.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎች ሆይ! እውነቱ ከጌታችሁ መጣላችሁ። በእርሱ የተመራም ሰው የሚመራው ለራሱ ነው። የተሳሳተም ሰው የሚሳሳተው ጉዳቱ በራሱ ላይ ብቻ ነው። እኔም በእናንተ ላይ ተጠባባቂ አይደለሁም በላቸው።

وَٱتَّبِعۡ مَا يُوحَىٰٓ إِلَيۡكَ وَٱصۡبِرۡ حَتَّىٰ يَحۡكُمَ ٱللَّهُۚ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلۡحَٰكِمِينَ ١٠٩

**109.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ አንተ የሚወረደውን ነገር ቁርኣንን ብቻ ተከተል። አላህ በእነርሱና በአንተ መካከል ባለው ጉዳይ ላይ እስከሚፈርድ ድረስ ታገሥ። እርሱም ከፈራጆቹ ሁሉ ብላጭ ነው።

**ከዩኑስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (98-109) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. አላህ በአዘል የጀሀነም ሰው መሆኑን ያረጋገጠበት ሰው ሁሉ ወደ እምነት ይመለስ ዘንድ መምከር እንደ ማይጠቅመው፤
2. በተለያየ ቦታና ጊዜ የሚነሱ የግፍ አራማጆች የሚጠብቃቸው ውርደትና ኪሣራ መሆኑንና ይህ ውርደትና የኪሣራ ቅጣት ቀደም በነበሩ የቀድሞ ግፈኞች ላይም ደርሶባቸው የነበረ መሆኑን፤
3. አላህ ሙስሊሞችን ለመርዳት የገባውን ቃል ከሓዲያንን ደምስሶ ሙስሊሞችን ነፃ በማውጣት የፈፀመው መሆኑን፤
4. ሰዎች ተጠራጠሩም አልተጠራጠሩም እውነት ምንጊዜም እውነት ሆኖ እንደሚቀጥል ሊተው የማይገባ ስለመሆኑ፤
5. ማጋራት እጅግ የተከለከለ ወንጀል መሆኑንና የሽርክ አራማጆችን ማግለል ግዴታ ስለመሆኑ፤
6. አላህ ይሁን ሲል የወሰነው ነገር በሙሉ የትኛውም ኃይል ሊያስቀረውና ሊያደናቅፈው የማይችል መሆኑን፤
7. የአላህን ፈጣሪነትና አምላክነት፤ የነብዩን (ﷺ) መልዕክተኛነት ያላረጋገጠ ሰው አማኝ ተብሎ የማይጠራ መሆኑን፤
8. ቁርኣን እና መልዕክተኛው ሙሐመድ (ﷺ) ይዘውት የመጡት የኢስላም ኃይማኖት ሐቅ መሆናቸውን፤
9. የሰው ልጅ ቅጣት የሚያገኘውም ሆነ ደስታን የሚጎናፀፈው በራሱ ተግባር መጥፎነትና መልካምነት መሆኑን፤
10. ቁርኣንና ሐዲስን መከተል በሙስሊሞች ላይ በሙሉ የተጣለ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
11. ትዕግስት ማድረግ ያለው ምንዳ ከፍተኛ መሆኑንና ለማንኛውም ችግር መፍትሔ የሚሰጠው አላህ ብቻ በመሆኑ መፍትሄን ከአላህ ብቻ መጠበቅ የግድ ስለመሆኑ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የዩኑስ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (11)
# የነብዩ ሁድ ምዕራፍ
# (ሱረቱ ሁድ)

سُورَةُ هُودٍ

## የወረደው በመካ ነው። አናቅፅ (123) ናቸው።
## የሱረቱ ሁድ መግቢያ

ይህን ስያሜ ያገኘው በ (98) ኛው አንቀፅ ላይ ታሪካቸው በተወሱት ነብይ በነብዩ ሁድ ስም ነው የተሰየመው።

ይህ ነብይ በቁርኣን ዉስጥ ሶስት ምእራፎች ላይ ሰባት ጊዜ በስም ተወስቷል።

ቁርኣንን በማሞገስና አምልኮ ለአንድ አላህ ብቻ መሆኑን በማስተማር፤

እንቢ ያለን ክፍል በቅጣት በማስፈራራት፤ እሺ ያለን ወገን ደግሞ በምህረት በማብሰር አስተምህሮቱን ይጀምራል።

ከዚያ በመቀጠል የአላህን ችሎታና ብቸኛ ጌታ መሆኑ፤ የሰው ልጆች የአላህን ፀጋም ሆነ ቁጣውን ሲቀበሉ የተለያዩ መሆናቸውን፤ ከዚያ የቁርኣንን ትልቅነትና በእሱ ዙሪያም ስለ ነበረው ፍልሚያና ከሓዲያን በእሱ ስለመካዳቸው ያወሳል።

ብዙ ነብያት ከየህዝቦቻቸው ጋር ያካሄዱትን ግብግብ እና አላህ በከሓዲያን ላይ በዚህ ዓለም ላይ እያሉ ምን ምን ዓይነት ቅጣት እንደ ወሰደባቸውና አማኞችን እንዴት ከዛ ቅጣት ነጻ እንዳወጣቸው አውስቶ፤ የነብዩ ኑህን ታሪክ በተለይ በሰፊው አውስቷል።

ከዚያ የቀሩትን ነብያት ታሪክ በአጭሩ አካትቷል። ከእነዚህ ታሪኮች የምንማራቸውን ብዙ እውነታዎች በማውሳት መልዕክቱን ያጠቃልላል። ይህ ምዕራፍ መካ ከወረዱ ምእራፎች አንዱ በመሆኑ አስተምህሮቱም በእነዚሁ በመካ ምእራፎች ላይ እንደ ሚነገረው ሁሉ ዐቂዳን በተመለከተ ሲሆን የቀደምት ነብያቶችን ታሪክ ከ (1-5) የሚሆኑትን ዋቢ አድርጎ አውስቷል።

ቲርሚዚና ሐኪም በዘገቡት ሐዲስ «አንድ ቀን አቡበክር ሲዲቅ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው «ሸበቱ እኮ» ሲሏቸው ጊዜ ሁድ፤ አል-ዋቂዐህ፤ አል-ሙርሰላህ፤ ዐመ የተሳአሉንና ኢዘ ሽምሹ ኩዊረት፤ ... የሚሉት ምእራፎች ናቸው ያሸበቱኝ በማለት መልሰውላቸዋል።»

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓرۚ كِتَٰبٌ أُحۡكِمَتۡ ءَايَٰتُهُۥ ثُمَّ فُصِّلَتۡ مِن لَّدُنۡ حَكِيمٍ خَبِيرٍ ١
أَلَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّا ٱللَّهَۚ إِنَّنِي لَكُم مِّنۡهُ نَذِيرٞ وَبَشِيرٞ ٢

**1-2.** አሊፍ፤ ላም፤ ራ፤* ይህ ቁርኣን አንቀጾቹ በጥንካሬ የተሰካኩ ከዚያም የተዘረዘሩ መጽሐፍ ነው። ጥበበኛ ውስጠ ዐዋቂ ከሆነው ከአላህ ዘንድ የተወረደ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህን እንጂ ሌላን አትገዙ። እኔ ለእናንተ ከእርሱ ዘንድ የተላኩ አስፈራሪና አብሳሪ ነኝ (በላቸው)።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَأَنِ ٱسۡتَغۡفِرُواْ رَبَّكُمۡ ثُمَّ تُوبُوٓاْ إِلَيۡهِ يُمَتِّعۡكُم مَّتَٰعًا حَسَنًا إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمّٗى وَيُؤۡتِ
كُلَّ ذِي فَضۡلٖ فَضۡلَهُۥۖ وَإِن تَوَلَّوۡاْ فَإِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٖ كَبِيرٍ ٣ إِلَى ٱللَّهِ
مَرۡجِعُكُمۡۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ٤

**3-4.** ጌታችሁን ምህረት ለምኑት። ከዚያ ወደ እርሱ ተመለሱ። እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ መልካምን መጥቀም ይጠቅማችኋልና ለትሩፋት ባለቤት ሁሉ ችሮታውን ይሰጠዋል። ብትሸሹም እኔ በእናንተ ላይ የታላቅን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ። መመለሻችሁ ወደ አላህ ብቻ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

أَلَآ إِنَّهُمۡ يَثۡنُونَ صُدُورَهُمۡ لِيَسۡتَخۡفُواْ مِنۡهُۚ أَلَا حِينَ يَسۡتَغۡشُونَ ثِيَابَهُمۡ يَعۡلَمُ مَا يُسِرُّونَ
وَمَا يُعۡلِنُونَۚ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٥

**5.** ንቁ! እነርሱ ከእርሱ ከአላህ ይደበቁ ዘንድ ደረቶቻቸውን ያጥፋሉ። ንቁ! ልብሶቻቸውን በሚከናነቡ ጊዜ የሚደብቁትንም ሆነ የሚገልፁትን ሁሉ ያውቃል። እርሱ በደረቶች ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ ነውና።

ከሁድ ምዕራፍ (5) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰዎች ሲፀዳዱም ሆነ የግብረስጋ ግንኙነት ሲያደርጉ ሰውነታቸው በስርአቱ ይሸፍኑ ስላልነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ሱዩጢ።

*وَمَا مِن دَآبَّةٍ فِى ٱلْأَرْضِ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِ رِزْقُهَا وَيَعْلَمُ مُسْتَقَرَّهَا وَمُسْتَوْدَعَهَا ۚ كُلٌّ فِى كِتَٰبٍ مُّبِينٍ ﴿٦﴾

6. *በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ያለና ማረፊያዋንም ሆነ መርጊያዋን የሚያውቅ ቢሆን እንጂ። ሁሉም ነገር ግልጽ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ ነው።

✷ ክፍል አስራ ሁለት

وَهُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ وَكَانَ عَرْشُهُۥ عَلَى ٱلْمَآءِ لِيَبْلُوَكُمْ أَيُّكُمْ أَحْسَنُ عَمَلًا ۗ وَلَئِن قُلْتَ إِنَّكُم مَّبْعُوثُونَ مِنۢ بَعْدِ ٱلْمَوْتِ لَيَقُولَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ إِنْ هَٰذَآ إِلَّا سِحْرٌ مُّبِينٌ ﴿٧﴾ وَلَئِنْ أَخَّرْنَا عَنْهُمُ ٱلْعَذَابَ إِلَىٰٓ أُمَّةٍ مَّعْدُودَةٍ لَّيَقُولُنَّ مَا يَحْبِسُهُۥٓ ۗ أَلَا يَوْمَ يَأْتِيهِمْ لَيْسَ مَصْرُوفًا عَنْهُمْ وَحَاقَ بِهِم مَّا كَانُوا۟ بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿٨﴾

7-8. እርሱ (አላህ) ያ! ሰማያትንና ምድርን በስድስት* ቀናት ውስጥ የፈጠረ ነው። ዐርሹም በውሃ ላይ ነበር። የትኛችሁ ስራችሁ ያማረ መሆኑ ይፈትናችሁ ዘንድ ፈጠራችሁ። «እናንተ ከሞት በኋላ በእርግጥ ተቀስቃሾች ናችሁ» ብትልም እነዚያ የካዱት ይህ ግልፅ ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም ይላሉ። ቅጣቱንም ለተቆጠሩ ጥቂት ጊዜያቶች ከእነርሱ ብናቆይላቸው ከመውረድ የሚከለክለው ምንድን ነው? ይላሉ። ንቁ! በሚመጣባቸው ቀን ከእነርሱ ላይ ተመላሽ አይደለም። በእርሱ ይሳለቁበት የነበሩትም ቅጣት በእነርሱ ላይ ይወርድባቸዋል።

✷ «በስድስት ቀናት» የሚለው ቃል ምድራዊ ቀናትን እንደማያመለክት ግልፅ ነው። የምድር ቀናት ምድር ከተፈጠረች በኋላ የተፈጠሩና ምድር በእራሷ ዛቢያ የምታደርገው ውጤቶች ናቸው። እነዚህ ቀናቶች ግን ከዚህ የተለዩ ቀናት ናቸው። የአላህ ቀናት በአልሐጅ (47) ኛ አንቀፅ ላይ የአላህ አንድ ቀን የምድራዊውን ቀን አንድ ሺህ ዓመት እንደሚመጥን በአል. መዓሪጅ (4) ኛው አንቀፅ ላይ ደግሞ (50) ሺህ ዓመት ያህል መሆኑን እነዚህ ቀናት የሰው ልጅ ለጊዜው መቁጠሪያነት ከሚጠቀምባቸው ቀናት የተለዩ መሆናቸውን ያመለክታል።

ይህም ሰማይና ምድር የአሁኑን ቅርፅና ባህሪያቸውን ይዘው ለዐለሙ ከመገለጻቸው በፊት ውሃ እንደነበርና የአላህ ዐርሽም ከዚያ ውሃ ላይ እንደነበር ነው የሚያመለክተው። ይህን የሚመለከት በቁርኣንም በሐዲስም ተጨማሪ ማብራሪያ ያልተሰጠ መሆኑ ሩቅ ምስጢር ነውና ከዚህ በላይ ማለት የሚቻልበት ሁኔታ የለም። ሰማይና ምድሩን የፈጠረ ዩኒቨርሱን በስርዓት የሚመራ አምላክ ሙታንን ይቀሰቅሳል መባሉ የሚደንቅ አልነበረም። በቀላሉ ሊቀበሉት የሚገባ እውነት ነው። ግና ከሓዲያን ይህ ይደንቃቸዋል። ይገርማቸዋል። ቅዠትም ይመስላቸዋል።

ከሁድ ምዕራፍ (8) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በሱረቱ ኢቅተረበ አንደኛ ተራ ቁጥር ላይ ያለው አንቀፅ ሲወርድ ሰዎች ቂያማ የቀረበ በመሆኑ ከብዙ ነገሮች ከተቆጠቡ በኋላ እንደገና ወደ ነበሩበት መጥፎ ነገር በመመለሳቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ሱዩጢ)

وَلَئِنْ أَذَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ مِنَّا رَحْمَةً ثُمَّ نَزَعْنَٰهَا مِنْهُ إِنَّهُۥ لَيَـُٔوسٌ كَفُورٌ ٩ وَلَئِنْ أَذَقْنَٰهُ نَعْمَآءَ
بَعْدَ ضَرَّآءَ مَسَّتْهُ لَيَقُولَنَّ ذَهَبَ ٱلسَّيِّـَٔاتُ عَنِّىٓ ۚ إِنَّهُۥ لَفَرِحٌ فَخُورٌ ١٠ إِلَّا ٱلَّذِينَ صَبَرُوا۟
وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُم مَّغْفِرَةٌ وَأَجْرٌ كَبِيرٌ ١١

**9-11.** ሰውን ከኛ ከችሮታችን ብናቀምሰውና ከዚያ ብንወስድበት እርሱ ተስፋ ቆራጭና ክህደተ ብርቱ ነው፡፡ ካገኘችው ችግር በኋላ ፀጋዎቻችንን ብናቀምሰው ችግሮች ከእኔ ላይ ተወገዱ ይላል፡፡ አያመሰግንም፡፡ እርሱ ተደሳችና ጉረኛ ነውና፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ) እነዚያ የታገሱና መልካም ሥራዎችን የሰሩ ሁሉ እነዚያ ለእነርሱ ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው፡፡

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-11) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ቁርአን ለነብዩ ሙሐሙድ (ﷺ) ከተሰጡት ነገሮች በሙሉ ተዐምራዊነቱ ኃያል የሆነ መፅሐፍ እንደሆነ፤
2. ሰማያዊ መፅሀፍና አናቅፅ ወደዚህ ምድር የመውረዳቸው አብይ አላማና ዋና ምክንያት የሰው ልጅ አላህን ብቻ ይገዛ ዘንድ በተለይም ከሓዲያን ከጥፋታቸው በመመለስ ይቅርታ እንዲጠይቁ ለማስተማር መሆኑን፤
3. ማንኛውም ዒባዳ ተቀባይነት የሚኖረው ሽርክን በአላህ ማጋራትን ካስወገድን በኋላ ዒባዳ ለመስራት ከሽርክ ነፃ መሆን ቅድሚያ እንደሚሰጠው፤
4. መልካም ሥራ ምን ጊዜም ተውሒድን ለያዙ ሰዎች አትራፊ የሚያደርግ እንጂ ምንም አክሳሪ አለመሆኑን፤
5. ከአላህ ለመደበቅ በማሰብ በልባቸው ውስጥ ክህደታቸውን ይሸሽጉ የነበሩ ቀደምት ከሓዲያን ምን ያህል በድንቁርና ማዕበል የተወጡ እንደነበሩ፤
6. ከኃጢአትና ከአጋሪነት ነጻ ለመሆን ወደ አላህ መመለስና ለእርሱ ብቻ ማደር መሆኑን፤
7. መልካም ሠሪዎች በዚህች ዓለም የሚጎናፀፉት ስክነትና ደስታ በመጭው ዓለም የሚያገኙት ምንዳና ተድላ ምን እንደሚመስል፤
8. የሰው ልጅ ወደደም ጠላም ወደ አላህ መመለሱና ከዚያም ፍትህን ከአላህ መሰጠቱ የማይቀር መሆኑን፤
9. የአላህ እውቀት ጥልቅና ስር የሰደደ ከመሆኑም ባሻገር እርሱ ፍጡራኑን በሙሉ የመቀለብና የመንከባከብ ኃላፊነት የወሰደ ጌታ ስለ መሆኑ፤
10. አላህ ፍጡራኑን ለምን ዓላማና ምክንያት እንደፈጠራቸው የሚያስተምር ቁርአናዊ አስተምህሮት፤
11. የአላህን ብቸኛ አምላክነት ማረጋገትና በኋላ ሙቶ የመነሣትና ዳግም ሕይወት የመኖሩን ሃቅ ማረጋገጥ፤
12. አላህ ወንጀልን ስንሰራ በቶሎ የቅጣት እርምጃ ያለመውሰዱ ሊያሞኘንና በኃጢአታችንና በስህተታችን እንድንቀጥል ሊያደርገን እንደማይገባ፤
13. የሰው ልጅ ታሪክ ስንፈትሽ እምነትን ከመጨበጡ በፊት ያለው ታሪኩ በውርደት፤ በሞራልና በአስተሳሰብ ዝቅጠት የተሞላ እንደነበር፤
14. ከአላህ እዝነት ተስፋን መቁረጥ ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
15. ለምድራዊ ሕይወት ብልጭልጭ ነገሮች ልብን ሰጥቶ በደስታ ሃሴት ማድረግ ተገቢ ያለመሆኑን፤
16. የትዕግስተኛ ሙእሚን መንፈስ ምን ያህል በመንፈሳዊ እርካታ የተሞላ እንደሆነ እንማራለን፡፡

فَلَعَلَّكَ تَارِكُۢ بَعۡضَ مَا يُوحَىٰٓ إِلَيۡكَ وَضَآئِقُۢ بِهِۦ صَدۡرُكَ أَن يَقُولُواْ لَوۡلَآ أُنزِلَ عَلَيۡهِ كَنزٌ
أَوۡ جَآءَ مَعَهُۥ مَلَكٌۚ إِنَّمَآ أَنتَ نَذِيرٞۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ وَكِيلٌ ١٢ أَمۡ يَقُولُونَ ٱفۡتَرَىٰهُۖ
قُلۡ فَأۡتُواْ بِعَشۡرِ سُوَرٖ مِّثۡلِهِۦ مُفۡتَرَيَٰتٖ وَٱدۡعُواْ مَنِ ٱسۡتَطَعۡتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ إِن كُنتُمۡ
صَٰدِقِينَ ١٣ فَإِلَّمۡ يَسۡتَجِيبُواْ لَكُمۡ فَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّمَآ أُنزِلَ بِعِلۡمِ ٱللَّهِ وَأَن لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ فَهَلۡ
أَنتُم مُّسۡلِمُونَ ١٤

**12-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርሱ ላይ የገንዘብ ድልብ ለምን አልተወረደም? ወይም ከርሱ ጋር መልአክ ለምን አልመጣም? ማለታቸውን በመፍራት ወደ አንተ ከሚወርደው ከፊሉን ልትተው በእርሱም ልብህ ጠባብ ሊሆን ይፈራልሃል። አንተ አስፈራሪ ብቻ ነህ። አላህ በሁሉ ነገር ላይ (ወኪል) ተጠባባቂ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይልቁንም ቁርኣንን ቀጣጠፈው ይላሉን? እውነተኞች እንደሆናችሁ ብጤው የሆኑን አስር የተቀጣጠፉ ሱራዎች እስቲ አምጡ። ከአላህም ሌላ የቻላችሁትን ረዳት ጥሩ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእናንተ ጥሪውን ባይቀበሏችሁ (ጣዖት አምላኪያን ሆይ!) የተወረደው በአላህ እውቀት ብቻ መሆኑንና ከእርሱ ሌላ አምላክ አለመኖሩንም እወቁ። እናም አትሰልሙምን? (ስለሙ በላቸው)።

مَن كَانَ يُرِيدُ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا وَزِينَتَهَا نُوَفِّ إِلَيۡهِمۡ أَعۡمَٰلَهُمۡ فِيهَا وَهُمۡ فِيهَا لَا يُبۡخَسُونَ ١٥
أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَيۡسَ لَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ إِلَّا ٱلنَّارُۖ وَحَبِطَ مَا صَنَعُواْ فِيهَا وَبَٰطِلٞ مَّا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٦

**15-16.** ቅርቢቱን ህይወትና ጌጧን የሚሹ የሆኑትን ሰዎች ሁሉ ሥራዎቻቸውን ምንዳዋን በእርሷ ውስጥ ወደ እነርሱ እንሞላላቸዋለን። እነርሱም በእርሷ ውስጥ ምንም አይጎድልባቸውም። እነዚያ እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ለእነርሱ ከእሳት በቀር የሌላቸው ናቸው። የሰሩትም ሥራ በእርሷ ውስጥ ተበላሸ። በቅርቢቱ ዓለም ይሰሩት የነበሩትም በጎ ሥራ ብልሹ ነው።

أَفَمَن كَانَ عَلَىٰ بَيِّنَةٖ مِّن رَّبِّهِۦ وَيَتۡلُوهُ شَاهِدٞ مِّنۡهُ وَمِن قَبۡلِهِۦ كِتَٰبُ مُوسَىٰٓ إِمَامٗا وَرَحۡمَةًۚ
أُوْلَٰٓئِكَ يُؤۡمِنُونَ بِهِۦۚ وَمَن يَكۡفُرۡ بِهِۦ مِنَ ٱلۡأَحۡزَابِ فَٱلنَّارُ مَوۡعِدُهُۥۚ فَلَا تَكُ فِي مِرۡيَةٖ مِّنۡهُۚ
إِنَّهُ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكَ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يُؤۡمِنُونَ ١٧

**17.** ከጌታው ዘንድ አስረጅ የደረሰውንና ከእርሱም የሆነ መስካሪ የሚከተለው (ከእርሱ) ከቁርኣን በፊትም የሙሳ መጽሐፍ መሪና እዝነት ሲሆን የመሰከረለት ሰውና የቅርቢቱን ህይወት እንደሚሻው ሰው ነውን? እነዚያ በርሱ (በቁርኣን) ያምናሉ። ከአህዛቦቹ በእርሱ የሚክድ ሰው ሁሉ መመለሻው እሳት ናት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእርሱም በመጠራጠር ውስጥ አትሁን። እሱ ከጌታህ ዘንድ የሆነ እውነት ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያምኑም።

وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ يُعْرَضُونَ عَلَىٰ رَبِّهِمْ وَيَقُولُ ٱلْأَشْهَـٰدُ
هَـٰٓؤُلَآءِ ٱلَّذِينَ كَذَبُوا۟ عَلَىٰ رَبِّهِمْ ۚ أَلَا لَعْنَةُ ٱللَّهِ عَلَى ٱلظَّـٰلِمِينَ ﴿١٨﴾ ٱلَّذِينَ يَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ
ٱللَّهِ وَيَبْغُونَهَا عِوَجًا وَهُم بِٱلْـَٔاخِرَةِ هُمْ كَـٰفِرُونَ ﴿١٩﴾ أُو۟لَـٰٓئِكَ لَمْ يَكُونُوا۟ مُعْجِزِينَ فِى
ٱلْأَرْضِ وَمَا كَانَ لَهُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ مِنْ أَوْلِيَآءَ ۘ يُضَـٰعَفُ لَهُمُ ٱلْعَذَابُ ۚ مَا كَانُوا۟ يَسْتَطِيعُونَ
ٱلسَّمْعَ وَمَا كَانُوا۟ يُبْصِرُونَ ﴿٢٠﴾ أُو۟لَـٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓا۟ أَنفُسَهُمْ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟
يَفْتَرُونَ ﴿٢١﴾ لَا جَرَمَ أَنَّهُمْ فِى ٱلْـَٔاخِرَةِ هُمُ ٱلْأَخْسَرُونَ ﴿٢٢﴾

**18-22.** በአላህ ላይ ውሸትን ከሚቀጣጥፉ ይበልጥ በዳይ ማነው? እነዚያ በጌታቸው ላይ ይቀረባሉ። መስካሪዎቹም እነዚህ በጌታቸው ላይ የዋሹት ሰዎች ናቸው ይላሉ። (ሙስሊሞች ሆይ)፣ ንቁ፣ የአላህ እርግማን በበዳዮች*1 ላይ ብቻ ይሁን።*2 እነሱም እነዚያ ከአላህ መንገድ ሰዎችን የሚከለክሉ የአላህን መንገድ መጥመሟንም የሚሹት እነርሱ ብቻ ናቸው። እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ከሓዲያን ናቸው። እነዚያ በምድር ውስጥ ከአላህ የሚያመልጡ አልነበሩም። ከአላህ ሌላ ለእነርሱ ረዳቶች አልነበሯቸውም። ለእነርሱ ቅጣቱ ይደራረብላቸዋል። እውነትን መስማትን የሚችሉ አልነበሩም። የሚያዩም አልነበሩም። እነዚያ እነርሱ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩና ይቀጣጥፉት የነበሩት ነገር የጠፋባቸው ናቸው። እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም በጣም ከሳሪዎቹ እነርሱ ብቻ መሆናቸው ጥርጥር የለውም።

*1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሰፍዋን ኢብኑ ሙሕሪዝ እንዳስተላለፉት: ኢብኑ ዑመር ጠዋፍ እያደረጉ ሳለ አንድ ሰው ወደርሳቸው መጣና «አቡ ዐብዱረህማን ሆይ! ወይም የዑመር ልጅ ሆይ! ነብዩ ስለ ነጅዋ አንዳች ነገር ሲሉ አልሰማህምን?» ሲል ጠየቃቸው። እሳቸውም «ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፤ ሙእሚን የሆነ ሰው ወደ አላህ ይቃረብና...»

(ሂሻም የተባለ ሌላ የሐዲሱ አስተላለፊ እንዳስተላለፈው) «ሙእሚን የሆነ ሰው በጌታው ስር እስከሆነ ድረስ ወደ ጌታው ይቃረባል። አላህም ኃጢአቶቹን እንዲናዘዝ ያደርገዋል። አላህ ሰውየውን «እንዲህ እንዲህ ያሉ ኃጢአቶች መስራትህን ታውቃለህን?» ብሎ ይጠይቀዋል። ሰውየውም ሁለት

ጊዜ «አዎ ሰርቻለሁ» ይላል። አላህም «በምድር ላይ ደብቄያችሁ ነበር። አሁን ደግሞ እምርልሃለሁ» ይለዋል። ከዚያ የመልካም ተግባራቱ መዝገብ ይዘጋል። ሌሎች ወይም ከሓዲያን ግን ምስክሮች ባሉበት ይጠራሉ። «እነዚህ በጌታቸው ላይ የዋሹ ሰዎች ናቸው» በማለትም ሚስጢራቸውን በአደባባይ ይናገራል፤ «ነጅዋ» ማለት በትንሳኤ ዕለት በአላህና በባሪያው መካከል የሚደረግ ግላዊ ንግግር ማለት ነው። (ሚስጢራዊ ንግግር ማለት ነው።)

✷2 ቡኻሪና ሙስሊም ዐብደላህ ቢን ዑመርን ዋቢ አድርገው በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ)፡- «አላህ የቂያማ ዕለት ትክክለኛ አማኝን ያቀርብና ለብቻው ያስቀምጠዋል። ከሰዎችም ይደብቀዋል። በጥፋቱም ይህን አላደረክም ይህን ስራህን አታውቀውም እያለ በመጠየቅ ያስተማምነዋል። እሱም አዎ አውቀዋለሁ። እናያለን ሁሉን ጥፋቱን በማመን እራሱን እንዳጠፋ ሲያረጋግጥ እኔ ግን በዱንያ እያለህ የደበኩልህ ዛሬም እምርሃለሁ ይለውና የኸይር ስራው መዝገብ ይሰጠዋል። ከሃዲና አስመሳዮች በእነሱ ላይ የሚመሰክሩት መስካሪዎችም እነዚህ በጌታቸው ላይ የዋሹት ሰዎች ናቸው ይላሉ። ንቁ የአላህ እርግማን በበዳዮች ላይ ይሁን ይባላል» ብለዋል።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَأَخۡبَتُوٓاْ إِلَىٰ رَبِّهِمۡ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٢٣

23. እነዚያ ያመኑትና በጎ ሥራዎችን የሠሩት ወደ ጌታቸውም የተዋረዱት የፈሩት እነዚያ የገነት ሰዎች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘላለም ዘውታሪዎች ናቸው።

۞ مَثَلُ ٱلۡفَرِيقَيۡنِ كَٱلۡأَعۡمَىٰ وَٱلۡأَصَمِّ وَٱلۡبَصِيرِ وَٱلسَّمِيعِۚ هَلۡ يَسۡتَوِيَانِ مَثَلًاۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ٢٤

24. የሁለቱ ክፍሎች ምሳሌ አይኑ የማያይ አይነ ስውር፤ ጆሮው የማይሰማ ደንቆሮ ሰውና አይኑ የሚያይ ጆሮው የሚሰማ ሰው ብጤ ነው። ሁለቱ በምሳሌነት ይስተካከላሉን? አትገሰፁንም?

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (12-24) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ለነብዩ (ﷺ) ያደርግላቸው የነበረው እንክብካቤና ድጋፍ እንዴት እንደነበር፤
2. ከሓዲያን ሕይወታቸው በሙሉ በትዕቢትና በክህደት የተሞላ እንደነበር፤
3. ነብዩ (ﷺ) ሰዎችን ማስተማርና ማስጠንቀቅ እንጂ ወደ ቀናው መንገድ እንዲገቡ ልባዊን ፍራቻን መፍጠር አለመሆኑን፤
4. ከሓዲያን በሙሉ ተሰባስበው አስር ምዕራፎችን የሚስተካከል ለማምጣት ከቻሉ ይሞክሩ ዘንድ መጋበዛቸውን፤
5. ለዚሁ ተግባር ከራሳቸው አልፈው በአማልክቶቻቸው ታግዘውም ማድረግ ካልቻሉ ሁለት ነገሮችን መቀበላቸው የግድ መሆኑን፤
6. ቁርኣን የሰብአዊ ፍጡር ጭንቅላት ውጤት እንዳልሆነና በአላህ እውቀት እንደወረደ፤
7. አማልክቶቻቸው ይህን መሥራት ተስናቸዋልና ከሓዲያን እንደሚያስቧቸው ኃይልና ስልጣን ያላቸው እንዳልሆኑ፤
8. ከሃዲ ምንም እንኳን በአላህ ያላመነ ቢሆንም ለምድራዊ ሕይወቱ መጠቃቀሚያ ሰርቶ የመብላት መብት የተሰጠው መሆኑን፤

9. ከሃዲ መልካም ስራዎችን ቢሰራም በመልካም ስራዎቹ ምድራዊ ምንዳን ሊያገኝ እንደሚችል ሆኖም በመጨረሻው ሕይወት ምንም ምንዳ የማያገኝበት መሆኑን፤
10. ሙስሊሞች ሀይማኖታዊ ህግጋቶችንና ድንጋጌዎችን ለመፈፀም የሚያስችሉ ብቁ ማስረጃዎች ያሏቸው መሆኑንና በአንፃሩም ሌሎች አመለካከቶችና እምነቶችን የሚከተሉ ሰዎች ግን ለሚሰሩት ሁሉ ብቁ የሆነ ማስረጃ ማቅረብ የማይችሉ በስሜትና በድንቁርና የሚዋልሉ ስለመሆናቸው፤
11. የሰው ልጆች ብዙ ጊዜ ከትክክለኛው ጎዳና የሚያፈነግጡ ስለመሆኑና ብዙዎቹ ሰዎች ትክክለኛው እምነትን እንደማይከተሉ የተረጋገጠ መሆኑን፤
12. ከሰዎች ብዙዎች ትክክለኛ አማኝ እንዳልሆኑ፤
13. ሁለት ተቃራኒ ነገሮችን እያነፃፀሩ መመልከቱና ተመሳሳይነታቸውንና ልዩነታቸውን እየገመገሙ መረዳት ተገቢ መሆኑን፤
14. ከሃዲ መንፈሱ እጅግ የዘቀጠ ከመሆኑም ባሻገር እውነቱን የመቀበል ብቃቱ የሞተ ስለሆነ ሐቅን ለማየትም ሆነ ለመስማት አይፈልግም። በአንፃሩ ሙስሊም ደግሞ መንፈሱ ብሩህ ልቡ ደግሞ ለእውነት የተከፈተ በመሆኑ ሐቅን የሚያይና ሐቅን የሚያዳምጥ መሆኑን፤
15. ሙዕሚኖች የጀነት ወራሾች መሆናቸውንና ከሓዲያን ደግሞ በአንፃሩ የገሀነም ወራሽ መሆናቸውን እንማራለን።

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦٓ إِنِّي لَكُمۡ نَذِيرٞ مُّبِينٌ ﴿٢٥﴾ أَن لَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّا ٱللَّهَۖ إِنِّيٓ أَخَافُ
عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٍ أَلِيمٖ ﴿٢٦﴾ فَقَالَ ٱلۡمَلَأُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن قَوۡمِهِۦ مَا نَرَىٰكَ إِلَّا بَشَرٗا
مِّثۡلَنَا وَمَا نَرَىٰكَ ٱتَّبَعَكَ إِلَّا ٱلَّذِينَ هُمۡ أَرَاذِلُنَا بَادِيَ ٱلرَّأۡيِ وَمَا نَرَىٰ لَكُمۡ عَلَيۡنَا مِن
فَضۡلِۭ بَلۡ نَظُنُّكُمۡ كَٰذِبِينَ ﴿٢٧﴾ قَالَ يَٰقَوۡمِ أَرَءَيۡتُمۡ إِن كُنتُ عَلَىٰ بَيِّنَةٖ مِّن رَّبِّي وَءَاتَىٰنِي
رَحۡمَةٗ مِّنۡ عِندِهِۦ فَعُمِّيَتۡ عَلَيۡكُمۡ أَنُلۡزِمُكُمُوهَا وَأَنتُمۡ لَهَا كَٰرِهُونَ ﴿٢٨﴾ وَيَٰقَوۡمِ
لَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مَالًاۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِۚ وَمَآ أَنَا۠ بِطَارِدِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْۚ إِنَّهُم مُّلَٰقُواْ
رَبِّهِمۡ وَلَٰكِنِّيٓ أَرَىٰكُمۡ قَوۡمٗا تَجۡهَلُونَ ﴿٢٩﴾ وَيَٰقَوۡمِ مَن يَنصُرُنِي مِنَ ٱللَّهِ إِن طَرَدتُّهُمۡۚ
أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٣٠﴾ وَلَآ أَقُولُ لَكُمۡ عِندِي خَزَآئِنُ ٱللَّهِ وَلَآ أَعۡلَمُ ٱلۡغَيۡبَ وَلَآ أَقُولُ إِنِّي
مَلَكٞ وَلَآ أَقُولُ لِلَّذِينَ تَزۡدَرِيٓ أَعۡيُنُكُمۡ لَن يُؤۡتِيَهُمُ ٱللَّهُ خَيۡرًاۖ ٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا فِيٓ أَنفُسِهِمۡ
إِنِّيٓ إِذٗا لَّمِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٣١﴾ قَالُواْ يَٰنُوحُ قَدۡ جَٰدَلۡتَنَا فَأَكۡثَرۡتَ جِدَٰلَنَا فَأۡتِنَا بِمَا تَعِدُنَآ إِن
كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴿٣٢﴾ قَالَ إِنَّمَا يَأۡتِيكُم بِهِ ٱللَّهُ إِن شَآءَ وَمَآ أَنتُم بِمُعۡجِزِينَ ﴿٣٣﴾
وَلَا يَنفَعُكُمۡ نُصۡحِيٓ إِنۡ أَرَدتُّ أَنۡ أَنصَحَ لَكُمۡ إِن كَانَ ٱللَّهُ يُرِيدُ أَن يُغۡوِيَكُمۡۚ
هُوَ رَبُّكُمۡ وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ﴿٣٤﴾

**25-34.** ነብዩ ኑሕን* ወደ ህዝቦቹ ላክንና አላቸውም። እኔ ለእናንተ ግልጽ አስፈራሪ ነኝ። አላቸው። አላህን እንጂ ሌላን አትገዙ። እኔ ለእናንተ የአሳማሚን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁና። ከህዝቦቹም መካከል እነዚያ በአላህ የካዱት ክፍሎች መሪዎች ብጤያችን ሰው ሆነህ እንጂ አናይህም። እነዚያም እነርሱ ሐሳበ ጥሬዎች የሆኑት ወራዶቻችን እንጂ ሌላ ተከትሎህ አናይህም። ለእናንተም በእኛ ላይ ምንም ብልጫን አናይም። ከቶውንም ውሸታሞች መሆናችሁን እንጠረጥራችኋለን አሉ። ህዝቦቼ ሆይ፣ እስቲ ንገሩኝ ከጌታዬ በግልጽ ማስረጃ ላይ ብሆን እና ከእርሱም ዘንድ የሆነን ችሮታ ነብይነት ቢሰጠኝና በእናንተ ላይ ግን ይህች እውነታ ብትደበቅባችሁ እናንተ ለእርሷ ጠይዎች ስትሆኑ እርሷን በመቀበል እናስገድዳችኋለን? አላቸው። ህዝቦቼ ሆይ፣ በእርሱ (በተላከሁበት ማድረስ) ላይ ገንዘብን አልጠይቃችሁም። ምንዳዬ በአላህ ላይ እንጂ ከሌላ አይደለም። እኔም እነዚያን በአላህ ያመኑትን አባራሪ አይደለሁም። እነርሱ ከጌታቸው ጋር የሚገናኙ ናቸውና። ግን እኔም የምትሳሳቱ ህዝቦች ሆናችሁ አያችኋለሁ። ህዝቦቸም ሆይ!፣ ባባርራቸው ከአላህ ቅጣት የሚያድነኝ ማን ነው? አትገሰፁምን? እኔ ዘንድ የአላህ ግምጃ ቤቶች አሉ። ሩቅንም አውቃለሁ አልላችሁም። እኔም መልአክ ነኝ አልላችሁም። ለእነዚያም ዓይኖቻችሁ ለሚያዋርዷቸው አላህ ደግ ነገርን (እምነትን) አይሰጣቸውም አልልም። አላህ በነፍሶቻቸው ውስጥ ያለውን ሁሉ ነገር አዋቂ ነው። እኔ ያን ጊዜ ከበደለኞች እሆናለሁና (አላቸው)። ኑህ ሆይ፣ በእርግጥ ተከራከርከን። እኛን መከራከርህንም አበዛህ። ከእውነተኞቹም ከሆንክ የምታስፈራራብንን ቅጣት አምጣው አሉ። እርሱን የሚያመጣባችሁ የፈለገ ከሆነ አላህ ብቻ ነው። እናንተም የምታቅቱት አይደላችሁም አላቸው። ኑህም ለህዝቦቹ ለእናንተም አላህ ሊያጠማችሁ ፈልጎ ከሆነ ልመክራችሁ ብፈልግም ምክሬ አይጠቅማችሁም። እርሱ ጌታችሁ ነው። ወደ እርሱም ብቻ ትመለሳላችሁ አላቸው።

* የነብዩ ኑህ ስምና ታሪክ በቁርኣን (43) ቦታ ላይ ተዘግቧል። በሰፊው የተወሳው በነብዩ ሁድ ምዕራፍ ላይ ነው። የሴቶች ምዕራፍ ላይ (163) ኛው አንቀፅና፤ ኣሊ. ዒምራን (33) ኛው አንቀፅ ላይ እንደምንመለከተው ሁሉ ለህዝቦቹ በግልፅ ተልኳል።

በአል አዕራፍ (59) ኛው፤ በኑህ (66) (21) ኛው አንቀፅ፤ በአል -አንከቡት (14) ኛው አንቀፅ፤ በሁድ (25) ኛው አንቀፅ ለ (950) ዓመት ያህል ወደ አላህ መንገድ ጠራቸው። በአል. አንከቡት (14) ኛው አንቀፅ ህዝቦቹ ግን አስተባበሉት። በአሽ. ሹራ (105-117) ኛው፤ በአል. አዕራፍ (60-64) ኛው፤ ልጁና ሚስቱም አልተቀበሉትም። በሁድ (42) ኛው፤ በአት. ተህሪም (10) ኛው አላህ ደግሞ በውሃ አስጠማቸው። በአል. ፉርቃን (37)፤ በአል. አዕራፍ (64) ኛው አንቀፅ እርሱ ደግሞ አመስጋኝ ባሪያ ተብሎ ተጠራ። በለሊት ጉዞ (3) ኛው አንቀፅ በአላህ ከተመረጡት አምስቱ ሩሱሎች አንዱ ነው። በአልአህዛብ (7) ኛው አንቀፅ ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን። በ (አስሷፋት (79) ኛው አንቀፅ)

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (25-34) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩ ኑህ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ በአላህ ማጋራት ወንጀል መተግበር ከጀመረ በኋላ ሕዝቡን ለማስጠንቀቅና ለማስተማር የተላኩ የመጀመሪያው መልዕክተኛ መሆናቸውን፤
2. አላህን እንጂ ሌላን አትገዙ ማለት «የላኢላሀ ኢለላሏህ» ትርጉም መሆኑን፤
3. የቂያማን ቀን ቅጣት ማስታወስ ተገቢ መሆኑን፤
4. ብዙ ጊዜ ለነብያት ጥሪ አወንታዊ ምላሽ የሚሰጡትና የነብያት ተከታዮች (ደቀመዛሙርት) የሚሆኑት የድሃው ህብረተሰብ ክፍል አባላት መሆናቸውንና በአንፃሩም ሀብታሞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ታላላቅ ሰዎች የነብያትን ጥሪ በመቃወም እንደሚሰለፉ፤
5. ኩራተኞች በተለያየ ነገር የሚያንሳቸውን ሰው ሲያጋጥማቸው የሚያሳዩት ንቀት ከፍተኛ መሆኑን፤
6. በአንድ ሰው ላይ ወይም በአንድ አካል ላይ ጥላቻ በሚያድርብን ጊዜ ማየትም ሆነ ድምፁን መስማት አለመፈለግ የሰዎች ተፈጥሮ እንደሆነ፤
7. ደካማዎችን መንከባከብና ለእነርሱም ክብር ማሳየት አስፈላጊና ግዴታ ስለመሆኑ፤
8. የሩቅና የተደበቀን ሚስጥር የሚያውቀው አንድ አላህ ብቻ መሆኑን፤
9. ማንኛውንም ሰው በንቀት መመልከት የተከለከለ መሆኑን፤
10. ሐቅን ለማጋለጥ እውነትን ለመግለፅ የሚደረግ ክርክር ጠቀሜታው የጎላ በመሆኑ መፈቀዱን፤
11. የአላህን ፍላጎት ከየትኛውም አካል ፍላጎት የበለጠና ያለምንም ጥርጥር ተፈፃሚ ማድረግ እንደሚገባ፤
12. አላህ ኸይርን ያልሻለት ሰው የማንም ምክር ሊመልሰውና ሊጠቅመው እንደማይችል፤
13. አንድ ሰው ከመሞቱ በፊትና ሃይማኖታዊ አቋሙን በተመለከተ ሙሉ ብይን ላይ ደርሶ መወሰኑ ተገቢ ያለመሆኑንና ሰው በሕይወት ላይ እስካለ ድረስ ተስፋ እንደማይቆረጥበት እንማራለን።

أَمۡ يَقُولُونَ ٱفۡتَرَىٰهُۖ قُلۡ إِنِ ٱفۡتَرَيۡتُهُۥ فَعَلَيَّ إِجۡرَامِي وَأَنَا۠ بَرِيٓءٞ مِّمَّا تُجۡرِمُونَ ﴿٣٥﴾ وَأُوحِيَ
إِلَىٰ نُوحٍ أَنَّهُۥ لَن يُؤۡمِنَ مِن قَوۡمِكَ إِلَّا مَن قَدۡ ءَامَنَ فَلَا تَبۡتَئِسۡ بِمَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ﴿٣٦﴾
وَٱصۡنَعِ ٱلۡفُلۡكَ بِأَعۡيُنِنَا وَوَحۡيِنَا وَلَا تُخَٰطِبۡنِي فِي ٱلَّذِينَ ظَلَمُوٓاْ إِنَّهُم مُّغۡرَقُونَ ﴿٣٧﴾ وَيَصۡنَعُ
ٱلۡفُلۡكَ وَكُلَّمَا مَرَّ عَلَيۡهِ مَلَأٞ مِّن قَوۡمِهِۦ سَخِرُواْ مِنۡهُۚ قَالَ إِن تَسۡخَرُواْ مِنَّا فَإِنَّا نَسۡخَرُ
مِنكُمۡ كَمَا تَسۡخَرُونَ ﴿٣٨﴾ فَسَوۡفَ تَعۡلَمُونَ مَن يَأۡتِيهِ عَذَابٞ يُخۡزِيهِ وَيَحِلُّ عَلَيۡهِ عَذَابٞ
مُّقِيمٌ ﴿٣٩﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَ أَمۡرُنَا وَفَارَ ٱلتَّنُّورُ قُلۡنَا ٱحۡمِلۡ فِيهَا مِن كُلّٖ زَوۡجَيۡنِ ٱثۡنَيۡنِ وَأَهۡلَكَ
إِلَّا مَن سَبَقَ عَلَيۡهِ ٱلۡقَوۡلُ وَمَنۡ ءَامَنَۚ وَمَآ ءَامَنَ مَعَهُۥٓ إِلَّا قَلِيلٞ ﴿٤٠﴾ ۞ وَقَالَ ٱرۡكَبُواْ فِيهَا
بِسۡمِ ٱللَّهِ مَجۡر۪ىٰهَا وَمُرۡسَىٰهَآۚ إِنَّ رَبِّي لَغَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٤١﴾

**35-41.** ይልቁንም ቀጠፈው ይላሉን? (ሙሐመድ ሆይ)፣ ብቀጥፈው ኃጢአቴ ቅጣቱ በእኔ ላይ ነው። እኔም ከምታጠፉት ጥፋት ንፁህ ነኝ በላቸው። ወደ ኑህም እነሆ ከህዝቦችህ ካመኑት በስተቀር ወደፊት ሌሎች አያምኑም። ይሠሩት በነበሩት ክህደት አትዘን ማለት ተወረደ። አላህም በጥበቃችንና በትዕዛዛችን ሆነህ መርከቢቱን ሥራ። በእነዚያም በበደሉት ሰዎች ነገር አታናግረኝ። እነርሱ የሚሰምጡ ናቸውና (አለው)። ከወገኖቹም መሪዎቹ በእርሱ አጠገብ ባለፉ ቁጥር በእርሱ እየተሳለቁ መርከቢቱን ይሠራል። በእኛ ብትሳለቁ እኛም እንደተሳለቃችሁብን በእናንተ እንሳለቅባችኋለን አላቸው። የሚያዋርደው ቅጣት የሚመጣበትን በእርሱም ላይ ዘውታሪ ቅጣት የሚሰፍርበትን ሰው ማንነት ወደ ፊት ታውቃላችሁ (አላቸው)። ትዕዛዛችንም በመጣና እቶኑም በገነፈለ ጊዜ መርከቧ ውስጥ ከየዓይነቱ ሁሉ ሁለት ሁለት (ወንድና ሴት) ቤተሰቦችህንም ቃል ያለፈበት ብቻ ሲቀር ያመነንም ሰው ሁሉ ጫን አልነው። ከእርሱም ጋር ጥቂቶች እንጂ አላመኑም ነበር። መሄዷም መቆሟም በአላህ ስም ነው እያላችሁ በእርሷ ተሳፈሩ። ጌታዬ መሓሪና አዛኝ ነውና አላቸው።

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (35-39) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ተንኮለኞች በሚሸርቡት ሤራና በሚጎነጉኑት ተንኮል ማዘንና መተከዝ አስፈላጊ አለ መሆኑን፤
2. መርከብ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው በነቢዩ ኑህ ዘመን መሆኑንና እርሳቸውም የመርከብ ስራን ሙያ የተማሩት በአላህ መልካም ፈቃደኝነትና በእርሱ አስተማሪነት መሆኑን፤
3. በሐቀኞች የአላህ ቅን ባሪያዎች ላይ የሚያፌዝና የሚያላግጥ ሰው መጨረሻው ውርደትና አሰቃቂ ቅጣት ስለመሆኑ፤
4. አላህ ለነብያት የገባላቸውን ቃል ኪዳን በሙሉ በተገቢው ጊዜና ቦታ ላይ ተፈፃሚ እያደረገ እንደነበር፤
5. ከሶስቱ ልጆቻቸው ሳም፤ ሓምና ያፌስ ከተባሉት ልጆቻቸው ከነሚስቶቻቸው ጋር ከሰማኒያ የማይበልጡ ሰዎች ናቸው አምነው የነበሩ።

وَهِىَ تَجْرِى بِهِمْ فِى مَوْجٍ كَٱلْجِبَالِ وَنَادَىٰ نُوحٌ ٱبْنَهُۥ وَكَانَ فِى مَعْزِلٍ يَٰبُنَىَّ ٱرْكَب مَّعَنَا
وَلَا تَكُن مَّعَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٤٢﴾ قَالَ سَـَٔاوِىٓ إِلَىٰ جَبَلٍ يَعْصِمُنِى مِنَ ٱلْمَآءِ ۚ قَالَ لَا عَاصِمَ
ٱلْيَوْمَ مِنْ أَمْرِ ٱللَّهِ إِلَّا مَن رَّحِمَ ۚ وَحَالَ بَيْنَهُمَا ٱلْمَوْجُ فَكَانَ مِنَ ٱلْمُغْرَقِينَ ﴿٤٣﴾ وَقِيلَ
يَٰٓأَرْضُ ٱبْلَعِى مَآءَكِ وَيَٰسَمَآءُ أَقْلِعِى وَغِيضَ ٱلْمَآءُ وَقُضِىَ ٱلْأَمْرُ وَٱسْتَوَتْ عَلَى ٱلْجُودِىِّ ۖ
وَقِيلَ بُعْدًا لِّلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٤٤﴾ وَنَادَىٰ نُوحٌ رَّبَّهُۥ فَقَالَ رَبِّ إِنَّ ٱبْنِى مِنْ أَهْلِى وَإِنَّ
وَعْدَكَ ٱلْحَقُّ وَأَنتَ أَحْكَمُ ٱلْحَٰكِمِينَ ﴿٤٥﴾

**42-45.** እርሷ እንደ ተራራዎች በሆነ ማዕበል ውስጥ እነርሱን ይዛቸው የምትንሻለል ስትሆን (በአላህ ስም ተቀመጡባት)። ኑህም ልጁን ከመርከቢቱ የራቀ ሆኖ ሳለ ልጄ ሆይ!፣ ከእኛ ጋር ተሳፈር። ከከሓዲያንም አትሁን ሲል ጠራው። ልጁም ከውሃው ወደሚጠብቀኝ ተራራ እጠጋለሁ አለ። አባቱም ዛሬ ከአላህ ትዕዛዝ ምንም ጠባቂ* የለም። (እርሱ ብቻ) ያዘነለት ካልሆነ በስተቀር አለው። ማዕበሉም በመካከላቸው ጋረደ። ልጁም ከሰማጮች ሆነ። ተባለም ምድር ሆይ፣ ወሀሽን ዋጪ። ሰማይ ሆይ፣ ዝናብሽን ያዢ። ውሃውም ሠረገ። ቅጣቱም ተፈፀመ። ጁዲይ በሚባለም ተራራ ላይ መርከቢቱ ተደላደለች። ለከሓዲያን ሰዎች ጥፋት ተገባቸው (ጥፉ) ተባለ። ነብዩ ኑህ ጌታውን- ጌታዬ ሆይ! ልጄ ከቤተሰቤ ነው። ቃል ኪዳንህም እውነት ነው። አንተም ከፈራጆች ሁሉ ይበልጥ ዐዋቂ ነህ በማለት ጠየቀ።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ መሪ ሁለት የአማካሪዎች ቡድን ካልኖሩት በስተቀር ለመሪነት አይመረጥም። አንደኛው ቡድን መልካም ነገር እንዲሰራ የሚያማክረው ይህንም መልካም ተግባር እንዲላመደው ምክር የሚሰጠው። ሁለተኛው ቡድን ደግሞ መጥፎ ስራ እንዲሰራና ይህንንም መጥፎ ስራ እንዲላመደው የሚመክረው። ከነዚህ ውስጥ ከስህተት የተጠበቀ ማለት አላህ የጠበቀው ብቻ ነው»

قَالَ يَٰنُوحُ إِنَّهُۥ لَيۡسَ مِنۡ أَهۡلِكَۖ إِنَّهُۥ عَمَلٌ غَيۡرُ صَٰلِحٖۖ فَلَا تَسۡـَٔلۡنِ مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٌۖ
إِنِّيٓ أَعِظُكَ أَن تَكُونَ مِنَ ٱلۡجَٰهِلِينَ ٤٦ قَالَ رَبِّ إِنِّيٓ أَعُوذُ بِكَ أَنۡ أَسۡـَٔلَكَ مَا لَيۡسَ لِي
بِهِۦ عِلۡمٌۖ وَإِلَّا تَغۡفِرۡ لِي وَتَرۡحَمۡنِيٓ أَكُن مِّنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٤٧ قِيلَ يَٰنُوحُ ٱهۡبِطۡ بِسَلَٰمٖ مِّنَّا
وَبَرَكَٰتٍ عَلَيۡكَ وَعَلَىٰٓ أُمَمٖ مِّمَّن مَّعَكَۚ وَأُمَمٞ سَنُمَتِّعُهُمۡ ثُمَّ يَمَسُّهُم مِّنَّا عَذَابٌ أَلِيمٞ ٤٨

**46-48.** አላህም ኑህ ሆይ!፣ እርሱ ከቤተሰብህ አይደለም። እርሱ መልካም ያልሆነ ስራ ነው። በእርሱ እውቀት የሌለህንም ነገር አትጠይቀኝ። እኔ ከሚሳሳቱት ሰዎች እንዳትሆን እገስጽሃለሁ አለው። ጌታዬ ሆይ፣ በእርሱ ለእኔ እውቀት የሌለኝን ነገር የምጠይቅህ ከመሆን እኔ በአንተ እጠበቃለሁ። ለእኔም ባትምረኝና ባታዝንልኝ ከከሳሪዎቹ እሆናለሁ አለ። ኑህ ሆይ፣ ከእኛ በሆነ ሰላም በአንተ ላይና አንተም ጋር ባሉት ህዝቦች ላይ በሆኑ በረከቶችም የተጎናፀፍክ ሆነህ ወደ ምድር ውረድ። ከነሱው ዘሮች የሆኑ ህዝቦችም በቅርቢቱ ዓለም በእርግጥ እናስመቻቻቸዋለን። ከዚያ ከእኛ የሆነ አሳማሚ ቅጣት ይደርስባቸዋል ተባለ።

تِلْكَ مِنْ أَنۢبَآءِ ٱلْغَيْبِ نُوحِيهَآ إِلَيْكَ ۖ مَا كُنتَ تَعْلَمُهَآ أَنتَ وَلَا قَوْمُكَ مِن قَبْلِ هَٰذَا ۖ
فَٱصْبِرْ ۖ إِنَّ ٱلْعَٰقِبَةَ لِلْمُتَّقِينَ ﴿٤٩﴾

**49.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ ከሩቁ ወሬዎች ወደ አንተ ያወረድነው ነው። አንተም ሆንክ ህዝቦችህ ከዚህ በፊት የምታውቁት አልነበራችሁም። ታገሥ ምስጉን የሆነችው ፍጻሜ ለሚጠነቀቁት ብቻ ናትና።

وَإِلَىٰ عَادٍ أَخَاهُمْ هُودًا ۚ قَالَ يَٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَٰهٍ غَيْرُهُۥٓ ۖ إِنْ أَنتُمْ إِلَّا
مُفْتَرُونَ ﴿٥٠﴾ يَٰقَوْمِ لَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا ۖ إِنْ أَجْرِىَ إِلَّا عَلَى ٱلَّذِى فَطَرَنِىٓ ۚ أَفَلَا
تَعْقِلُونَ ﴿٥١﴾ وَيَٰقَوْمِ ٱسْتَغْفِرُوا۟ رَبَّكُمْ ثُمَّ تُوبُوٓا۟ إِلَيْهِ يُرْسِلِ ٱلسَّمَآءَ عَلَيْكُم مِّدْرَارًا
وَيَزِدْكُمْ قُوَّةً إِلَىٰ قُوَّتِكُمْ وَلَا تَتَوَلَّوْا۟ مُجْرِمِينَ ﴿٥٢﴾ قَالُوا۟ يَٰهُودُ مَا جِئْتَنَا بِبَيِّنَةٍ وَمَا نَحْنُ
بِتَارِكِىٓ ءَالِهَتِنَا عَن قَوْلِكَ وَمَا نَحْنُ لَكَ بِمُؤْمِنِينَ ﴿٥٣﴾ إِن نَّقُولُ إِلَّا ٱعْتَرَىٰكَ بَعْضُ ءَالِهَتِنَا
بِسُوٓءٍ ۗ قَالَ إِنِّىٓ أُشْهِدُ ٱللَّهَ وَٱشْهَدُوٓا۟ أَنِّى بَرِىٓءٌ مِّمَّا تُشْرِكُونَ ﴿٥٤﴾ مِن دُونِهِۦ ۖ فَكِيدُونِى جَمِيعًا
ثُمَّ لَا تُنظِرُونِ ﴿٥٥﴾ إِنِّى تَوَكَّلْتُ عَلَى ٱللَّهِ رَبِّى وَرَبِّكُم ۚ مَّا مِن دَآبَّةٍ إِلَّا هُوَ ءَاخِذٌۢ بِنَاصِيَتِهَآ ۚ إِنَّ
رَبِّى عَلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٥٦﴾ فَإِن تَوَلَّوْا۟ فَقَدْ أَبْلَغْتُكُم مَّآ أُرْسِلْتُ بِهِۦٓ إِلَيْكُمْ ۚ وَيَسْتَخْلِفُ
رَبِّى قَوْمًا غَيْرَكُمْ وَلَا تَضُرُّونَهُۥ شَيْـًٔا ۚ إِنَّ رَبِّى عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ حَفِيظٌ ﴿٥٧﴾ وَلَمَّا جَآءَ أَمْرُنَا نَجَّيْنَا
هُودًا وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مَعَهُۥ بِرَحْمَةٍ مِّنَّا وَنَجَّيْنَٰهُم مِّنْ عَذَابٍ غَلِيظٍ ﴿٥٨﴾

**50-58.** ወደ ዓድ ወንድማቸውን*[1] ሁድን ላክን። አላቸው፡ ወገኖቼ ሆይ፣ አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ምንም አምላክ የላችሁም። እናንተ (ከአላህ ሌላ በማምለካችሁ) ቀጣፊዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም። ህዝቦቼ ሆይ!፣ በእርሱ በማድረሴ ላይ ምንዳን አልጠይቃችሁም። ምንዳዬ በዚያ በፈጠረኝ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም። አታውቁምን? ህዝቦቼ ሆይ!፣ ጌታችሁን ምህረትን ለምኑት። ከዚያም ወደ እርሱ ተፀፀቱ። ዝናብን በእናንተ ላይ ተከታታይ አድርጎ ይልክላችኋልና። ወደ ኃይላችሁም ሀይልን ይጨምርላችኋል። አመፀኞችም ሆናችሁ አትሽሹ። እነርሱም፡- ሁድ ሆይ!፣ በአስረጅ አልመጣህልንም። እኛም ለአንተ ንግግር ብለን አማልዕክቶቻችንን የምንተው አይደለንም። እኛም ለአንተ አማኞች አይደለንም አሉ። ከፊሎቹ አማልክቶቻችን በክፉ ነገር በዕብደት ለክፈውሃል እንጂ ሌላን አንልም (አሉ)። እኔ አላህን አስመሰክራለሁ።

ከምታጋሩትም እኔ ንፁህ መሆኔን መስክሩ አላቸው። ከእርሱ ሌላ (አማልክትን ከምታጋሩት ንፁህ ነኝ) ሁላችሁም ሆናችሁ ተንኮልን ሥሩብኝ ከዚያ አታቆዩኝ። እኔ ጌታዬና ጌታችሁ በሆነው በአላህ ላይ ብቻ ተመካሁ። በምድር ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም እርሱ አናትዋን የያዛት ብትሆን እንጂ። ጌታዬ ቃሉም ሥራውም በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነው አላቸው። ብትዞሩም ወደ እናንተ የተላኩበትን ነገር በእርግጥ አድርሼላችኋለሁ። ጌታዬም ከናንተ ሌላን ህዝብ ይተካል። ምንም አትጎዱትም። ጌታዬ በሁሉ ነገር ላይ ተጠባባቂ ነውና አላቸው። ትዕዛዛችን በመጣ ጊዜ ሁድንና እነዚያን ከእሱጋ ያመኑትን ከእኛ በሆነው ችሮታ አዳን። ከብርቱ ቅጣትም አዳናቸው።*2

*1 በዘር ሀረጋቸው ወንድማቸው ማለት እንጂ በሀይማኖት ማለት አይደለም።

*2 ይህ ታላቅ ነብይ ነብዩ ሁድ ምዕራፉ የተሰየመው በሳቸው ስም ነው። ስማቸው በቁርኣን ውስጥ ሰባት ጊዜ ተወስቷል። በአዕራፍ አንድ ጊዜ በ (65) ኛው አንቀፅ ላይ፤ በዚሁ አምስት ጊዜ በአንቀፅ (50)፤ (53)፤ (58)፤ (60)፤ (89) ኛውና፤ በአሽ. ሹዓራህ አንድ ጊዜ በአንቀፅ (189) ነው። በተለይ በዚሁ ስም በተሰየመው ላይ በሰፊው ተወስቷል።

**ከሁድ ምዕራፍ ከ (40-52) ካሉ አናቅፅ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፦**

1. ነብዩ (ﷺ) ያለፉት ህዝቦችን ታሪክ ለመተረክ መቻላቸው በራሱ ለነብይነታቸው በቂ ምስክር እንደሆነ፤
2. ማንም ሰው ራሱ በሰራው ወንጀል እንጂ በማንም ሰው ሥራ የማይጠየቅ ስለመሆኑ፤
3. እምነት ከቅጣትና ውርደት ነፃ የሚያደርግ ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ ሁሉ ክህደት ደግሞ ለጥፋት በር ከፋች ዋነኛ ምክንያት ነው።
4. በማንኛውም የመጓጓዣ አገልግሎት መስጫ (መኪና፤ አውሮፕላን፤ በቅሎ፤ ባቡር፤ መርከብና የመሳሰሉት) ላይ ለመሣፈር ሲንቀሳቀሱ ቢስሚላህ (በአላህ ስም) ማለት ተገቢ ስለ መሆኑ፤
5. የአባትና የእናትን ሐቅ ያለመጠበቅ ለጥፋት በር ከፋች መሆኑን፤
6. እምነትና የአላህን ፍራቻ መሠረት አድርጎ የሚፈጠሩ ግንኙነቶች በሙሉ ከዝምድና የተሻለ ትስስር የሚፈጥሩ መሆኑን፤
7. በእውቀት ላይ ያልተመሰረተ ተግባር ትክክል የመሆን ዕድሉ ጠባብ በመሆኑ የተከለከለ መሆኑን፤
8. ድንቁርናና መሃይምነት የተወገዙ ባህርያት መሆናቸውን፤
9. ነብዩ ኑህ ታላቅ ክብርና ማዕረግ የተሰጣቸው የአላህ መልዕክተኛ ስለመሆናቸው፤
10. ከቁርኣናዊ ተስተምህሮዎች የታሪክን ዘገባዎች መማር አስፈላጊነቱ የጎላ ስለመሆኑ፤
11. የነብዩ (ﷺ) ነብይነት ሐቅ መሆኑን፤
12. ትዕግስትና ሁሉንም ችሎ ማሳለፍ ከመልካም ስብዕናዎችና ከጥሩ ባህሪያት የሚመደብ ስለ መሆኑ፤
13. ቁርኣን በራዕይ ለነብዩ (ﷺ) የተገለፀ መሆኑን፤ አጋሪዎች ይህን ያስተባበሉ ነበር። ግና ይህ ታሪክ ሩቅ ሚስጥር ነው። ነብዩም ሕዝባቸውም አያውቁትም ነበር። እናም በዚህ መልኩ ለነብዩ (ﷺ) የተገለፀው በራዕይ አማካይነት ነው፤

14. ሁሉም ነብያት ያስተማሩት እምነት (ዐቂዳ) አንድ መሆኑን፤
15. ነብያት ለሕዝቦቻቸው ግልፅና የማያሻሙ መረጃዎችን ቢያቀርቡም ምንጊዜም ተቃዋሚ እንዳላጡ፤
16. ነብያት የሰጡት ማስጠንቀቂያና ያስተላለፉት መልዕክት እነርሱ እንዳሉት በተጨባጭ ተግባራዊ ሲሆን መታየቱ፤
17. የአላህ የማይለወጥ ውሳኔ፤ “መልካም ፍጻሜ የአማኞች ነው። ”ይህ መለኮታዊ መርህ ነው። አይሻርም። አይለወጥም፤
18. በሁሉም ዘመናትና ቦታዎች የተገኙና የሚገኙ አማኞች የጠበቀ ትስስር አንድ አምላክ፤ አንድ እምነት አንድ ዓላማና ተመሳሳይ ግብ እንዳላቸው፤
19. የነብዩ (ﷺ) ዘመን አጋሪዎች እና የቢድዐ አራማጅ ተባባሪዎቻቸው አላህ ባለዘዛቸው ጎዳና ላይ በመጓዙ ረገድ ተመሣሣይ የሆነ አካሄድ ያላቸው ህግ ወጦች መሆናቸውን፤
20. የአላህን ምህረት መፈለግና ንሰሀ መግባት (ተውበት ማድረግ) ያለው ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን፤
21. ምህረትን ለመለመን ከመናገር በፊት መቅደም ያለበት ተግባር መሆኑን እንማራለን።

وَتِلْكَ عَادٌۖ جَحَدُوا۟ بِـَٔايَـٰتِ رَبِّهِمْ وَعَصَوْا۟ رُسُلَهُۥ وَٱتَّبَعُوٓا۟ أَمْرَ كُلِّ جَبَّارٍ عَنِيدٍ ﴿٥٩﴾ وَأُتْبِعُوا۟
فِى هَـٰذِهِ ٱلدُّنْيَا لَعْنَةً وَيَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِۗ أَلَآ إِنَّ عَادًا كَفَرُوا۟ رَبَّهُمْۗ أَلَا بُعْدًا لِّعَادٍ قَوْمِ هُودٍ ﴿٦٠﴾

**59-60.** እነዚህ ነገዶች የዓድ ህዝቦች ናቸው። በጌታቸው ታዐምራት ካዱ። መልዕክተኞቹንም አመፁ። የኃያል ሞገደኛን ሁሉ ትዕዛዝም ተከተሉ። በዚች በቅርቢቱ ዓለምም እርግማን እንዲከተላቸው ተደረጉ። በትንሳኤም ቀን እንደዚሁ። ንቁ! ዓዶች ጌታቸውን ካዱ። ንቁ! የሁድ ህዝቦች ለሆኑት ዓዶች ከእዝነት መራቅ ይገባቸው።

۞ وَإِلَىٰ ثَمُودَ أَخَاهُمْ صَـٰلِحًاۚ قَالَ يَـٰقَوْمِ ٱعْبُدُوا۟ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنْ إِلَـٰهٍ غَيْرُهُۥۖ هُوَ أَنشَأَكُم
مِّنَ ٱلْأَرْضِ وَٱسْتَعْمَرَكُمْ فِيهَا فَٱسْتَغْفِرُوهُ ثُمَّ تُوبُوٓا۟ إِلَيْهِۚ إِنَّ رَبِّى قَرِيبٌ مُّجِيبٌ ﴿٦١﴾ قَالُوا۟
يَـٰصَـٰلِحُ قَدْ كُنتَ فِينَا مَرْجُوًّا قَبْلَ هَـٰذَآۖ أَتَنْهَىٰنَآ أَن نَّعْبُدَ مَا يَعْبُدُ ءَابَآؤُنَا وَإِنَّنَا لَفِى شَكٍّ
مِّمَّا تَدْعُونَآ إِلَيْهِ مُرِيبٍ ﴿٦٢﴾ قَالَ يَـٰقَوْمِ أَرَءَيْتُمْ إِن كُنتُ عَلَىٰ بَيِّنَةٍ مِّن رَّبِّى وَءَاتَىٰنِى مِنْهُ
رَحْمَةً فَمَن يَنصُرُنِى مِنَ ٱللَّهِ إِنْ عَصَيْتُهُۥۖ فَمَا تَزِيدُونَنِى غَيْرَ تَخْسِيرٍ ﴿٦٣﴾ وَيَـٰقَوْمِ هَـٰذِهِۦ
نَاقَةُ ٱللَّهِ لَكُمْ ءَايَةًۖ فَذَرُوهَا تَأْكُلْ فِىٓ أَرْضِ ٱللَّهِۖ وَلَا تَمَسُّوهَا بِسُوٓءٍ فَيَأْخُذَكُمْ عَذَابٌ
قَرِيبٌ ﴿٦٤﴾ فَعَقَرُوهَا فَقَالَ تَمَتَّعُوا۟ فِى دَارِكُمْ ثَلَـٰثَةَ أَيَّامٍۖ ذَٰلِكَ وَعْدٌ غَيْرُ مَكْذُوبٍ ﴿٦٥﴾
فَلَمَّا جَآءَ أَمْرُنَا نَجَّيْنَا صَـٰلِحًا وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مَعَهُۥ بِرَحْمَةٍ مِّنَّا وَمِنْ خِزْىِ يَوْمِئِذٍۚ
إِنَّ رَبَّكَ هُوَ ٱلْقَوِىُّ ٱلْعَزِيزُ ﴿٦٦﴾

**61-66.** ወደ ሠሙዶች ወንድማቸውን ሷሊህን ላክን። ህዝቦቼ ሆይ፣ አላህን ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ አምላክ የላችሁም። እርሱ በምድር ፈጠራችሁ። በውስጧ እንድታለሟትም አደረጋችሁ። ምህረቱንም ለምኑት። ከዚያ ወደ እርሱ ተመለሱ። ጌታዬ ለሁሉም ቅርብና (ለለመነው) ተቀባይ ነውና አላቸው። እነርሱም ሷሊህ ሆይ፣ ከዚህ በፊት በእኛ ውስጥ መሪ ልትሆን በእርግጥ የምትከጀል የነበርክ ስትሆን። አባቶቻችን የሚገዙትን ከመገዛት ትከለክለናለህን? እኛም ወደሱ ከምትጠራን ነገር በእርግጥ አወላዋይ በሆነ መጠራጠር ውስጥ ነን አሉ። ሷሊህም ህዝቦቼ ሆይ! እስቲ ንገሩኝ ከጌታዬ በሆነ ማስረጃ ላይ ብሆንና ከእርሱም የሆነን ችሮታ (ነብይነት) ቢሰጠኝና ባልታዘዘው ከአላህ ቅጣት የሚያድነኝ ማነው? ከማሳሳትም በስተቀር ምንም አትጨምሩልኝም አላቸው። ህዝቦቼ ሆይ! ይህች ለእናንተ ታአምር ስትሆን የአላህ ግመል ናት። ተዋትም በአላህ ምድር ውስጥ ትብላ። በክፉም አትንኳት ቅርብ የሆነ ቅጣት ያገኛችኋልና (አላቸው)። ወግተው ገደሏትም ሷሊህ በአገራችሁም ሶስትን ቀናት ብቻ ተጠቀሙ ይህ የማይዋሽ ቀጠሮ ነው አላቸው። እናም ትዕዛዛችን በመጣ ጊዜ ሷሊህንና እነዚያን ከእሱ ጋር ያመኑትን ከእኛ በሆነው እዝነት አዳን። ከዚያ ቀን ውርደት አዳናቸው። ጌታህ እርሱ ብርቱና አሸናፊ ነውና።

وَأَخَذَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ ٱلصَّيْحَةُ فَأَصْبَحُواْ فِي دِيَٰرِهِمْ جَٰثِمِينَ ﴿٦٧﴾ كَأَن لَّمْ يَغْنَوْاْ فِيهَآۗ
أَلَآ إِنَّ ثَمُودَاْ كَفَرُواْ رَبَّهُمْۗ أَلَا بُعْدًا لِّثَمُودَ ﴿٦٨﴾

**67-68.** እነዚያን የበደሉትንም ከባድ ጩኸት* ያዛቸው። በየቤቶቻቸውም ውስጥ የተንበረከኩ ሙት በድን ሆነው አደሩ። በእሷ ውስጥ እንዳልኖሩ ሆኑ። አስተውሉ ሠሙዶች ጌታቸውን በእርግጥ ካዱ። አስተውሉ ለሠሙዶች ከአላህ እዝነት መራቅ ተገባቸው።

* የጂብሪል ድምፅ ወይም ሌላ ከሰማይ የመጣ ጩኸት ነው።

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (53-68) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሓዲያን በተለያየ ቦታና ዘመን ቢኖሩም ሞገደኝነትና ትዕቢተኝነት የጋራ መለያቸው መሆኑን፣
2. ሙሽሪኮች ባህሪያቸው ተመሣሣይ፣ በእርኩስ መንፈስ የሚያምኑ፣ ሰውን ለማስፈራራት ሩሀኒይና አውሊያን የሚጠቀሙ መሆናቸውን፣
3. የነብያት ጥሪና የሚይዙት አቋም ተመሳሳይ መሆኑንና ነብዩ ኑህ ያራመዱትን አቋም ሁድም ሲያራምድ እንደነበር፣
4. ሁሉም ነገር ከአላህ ስልጣንና ቁጥጥር የማያልፍ ከእርሱም ችሎታ የማይዘል መሆኑን፣
5. አላህ በነብይነትና እነርሱንም በሚቃወሙ ኃይላት መሀከል ያስቀመጠው ድንጋጌ ይዘት፣
6. መልካም ሰዎች ባላቸው ግላዊ ስብዕና በቤተሰባቸው ዘንድ ቢከበሩም ኢስላማዊ ጥሪ ይዘው ሲመጡ ግን የሚያከብሯቸው ሰዎች እንኳን ሊጠሏቸውና ሊቃወሟቸው እንደሚነሱ፡

7. መጥፎ ሰዎችን በምንም መልኩ ቢሆን መታዘዝና መተባበር እንደማይገባ፤
8. ከሓዲያን ምንም እንኳ የጠየቁት ተአምር አላህ ቢያሣያቸውም ሊያምኑ እንደማይችሉ፤
9. የነብዩ ሷሊህ ለሕዝቦቻቸው ያሣዩት ተዐምር ከትላልቆቹ ተዐምራት የሚቆጠር ስለመሆኑና የነብዩ ሷሊህ ሕዝቦች ይህንን ታላቅ ተዐምር ቢያዩም ለማመን ግን እንዳልቻሉ፤
10. በአንድ ሀገር የሶስት ቀናት ቆይታ ማድረግ የሀገሩ ነዋሪ ነው የማያስብል መሆኑን፤
11. የግፍ መጨረሻው ውርደትና ክስረት መሆኑን እንማራለን።

وَلَقَدْ جَآءَتْ رُسُلُنَآ إِبْرَٰهِيمَ بِٱلْبُشْرَىٰ قَالُوا۟ سَلَـٰمًا ۖ قَالَ سَلَـٰمٌ ۖ فَمَا لَبِثَ أَن جَآءَ بِعِجْلٍ
حَنِيذٍ ﴿٦٩﴾ فَلَمَّا رَءَآ أَيْدِيَهُمْ لَا تَصِلُ إِلَيْهِ نَكِرَهُمْ وَأَوْجَسَ مِنْهُمْ خِيفَةً ۚ قَالُوا۟ لَا تَخَفْ
إِنَّآ أُرْسِلْنَآ إِلَىٰ قَوْمِ لُوطٍ ﴿٧٠﴾ وَٱمْرَأَتُهُۥ قَآئِمَةٌ فَضَحِكَتْ فَبَشَّرْنَـٰهَا بِإِسْحَـٰقَ وَمِن وَرَآءِ
إِسْحَـٰقَ يَعْقُوبَ ﴿٧١﴾ قَالَتْ يَـٰوَيْلَتَىٰٓ ءَأَلِدُ وَأَنَا۠ عَجُوزٌ وَهَـٰذَا بَعْلِى شَيْخًا ۖ إِنَّ هَـٰذَا لَشَىْءٌ
عَجِيبٌ ﴿٧٢﴾ قَالُوٓا۟ أَتَعْجَبِينَ مِنْ أَمْرِ ٱللَّهِ ۖ رَحْمَتُ ٱللَّهِ وَبَرَكَـٰتُهُۥ عَلَيْكُمْ أَهْلَ ٱلْبَيْتِ ۚ
إِنَّهُۥ حَمِيدٌ مَّجِيدٌ ﴿٧٣﴾ فَلَمَّا ذَهَبَ عَنْ إِبْرَٰهِيمَ ٱلرَّوْعُ وَجَآءَتْهُ ٱلْبُشْرَىٰ يُجَـٰدِلُنَا فِى قَوْمِ
لُوطٍ ﴿٧٤﴾ إِنَّ إِبْرَٰهِيمَ لَحَلِيمٌ أَوَّٰهٌ مُّنِيبٌ ﴿٧٥﴾ يَـٰٓإِبْرَٰهِيمُ أَعْرِضْ عَنْ هَـٰذَآ ۖ إِنَّهُۥ قَدْ جَآءَ أَمْرُ
رَبِّكَ ۖ وَإِنَّهُمْ ءَاتِيهِمْ عَذَابٌ غَيْرُ مَرْدُودٍ ﴿٧٦﴾

**69-76.** መልዕክተኞቻችን ወደ ኢብራሂም (በልጅ መውለድ) ብስራት መጡለትና ሰላም አሉት። እሱም ሰላም አላቸው። ጥቂትም ሳይቆይ ወዲያውኑ የተጠበሰን የወይፈን ስጋ አመጣ። እጆቻቸውም ወደ ምግቡ የማይደርሱ መሆናቸውን ባየ ጊዜ ተግባራቸው እንግዳ ሆነበት። ከእነርሱም ፍርሃት ተሰማው። አትፍራ እኛ ወደ ሉጥ ህዝቦች ተልከናልና አሉት። ሚስቱም ቁማ ነበርና ሳቀች። እናም በኢስሓቅ አበሰርናት። ከኢስሐቅም በኋላ በልጁ በየዕቁብ (አበሰርናት)። (እርሷም) ዋልኝ እኔ አሮጊት ይህም ባለቤቴ ሽማግሌ ሆኖ ሳለ እወልዳለሁን? ይህ በእርግጥ አስደናቂ ነገር ነው አለች።* በአላህ ትዕዛዝ ትደነቂያለሽን? አሏት። የኢብራሂም ቤተሰቦች ሆይ፣ የአላህ እዝነትና በረከት በእናንተ በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ ይሁን። እሱ ምስጉንና ለጋስ ነውና አሉ። ከኢብራሂም ፍራቻው በሄደለትና ብስራት በመጣችለት ጊዜ በሉጥ ህዝቦች ጉዳይ ይከራከረን ጀመር። ኢብራሂም በእርግጥ ታጋሽ፣ አልቃሻ እና መላሳ ነውና። ኢብራሂም ሆይ!፣ ይህን ክርክር ተው። እነሆ የጌታህ ትዕዛዝ በእርግጥ መጥቷል። እነርሱም የማይመለስ ቅጣት የሚመጣባቸው ናቸው (አሉት)።

* አንዳንድ የተፍሲር ሙሁሮች በዚህ ጊዜ ሳራ ዘጠና አመት ኢብራሂም ደግሞ መቶ ሃያ አመት ሁናቸው ነበር ይላሉ።

وَلَمَّا جَآءَتۡ رُسُلُنَا لُوطٗا سِيٓءَ بِهِمۡ وَضَاقَ بِهِمۡ ذَرۡعٗا وَقَالَ هَٰذَا يَوۡمٌ عَصِيبٞ ﴿٧٧﴾ وَجَآءَهُۥ
قَوۡمُهُۥ يُهۡرَعُونَ إِلَيۡهِ وَمِن قَبۡلُ كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٱلسَّيِّـَٔاتِۚ قَالَ يَٰقَوۡمِ هَٰٓؤُلَآءِ بَنَاتِي هُنَّ أَطۡهَرُ
لَكُمۡۖ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَلَا تُخۡزُونِ فِي ضَيۡفِيٓۖ أَلَيۡسَ مِنكُمۡ رَجُلٞ رَّشِيدٞ ﴿٧٨﴾ قَالُواْ لَقَدۡ عَلِمۡتَ
مَا لَنَا فِي بَنَاتِكَ مِنۡ حَقّٖ وَإِنَّكَ لَتَعۡلَمُ مَا نُرِيدُ ﴿٧٩﴾ قَالَ لَوۡ أَنَّ لِي بِكُمۡ قُوَّةً أَوۡ ءَاوِيٓ إِلَىٰ
رُكۡنٖ شَدِيدٖ ﴿٨٠﴾ قَالُواْ يَٰلُوطُ إِنَّا رُسُلُ رَبِّكَ لَن يَصِلُوٓاْ إِلَيۡكَۖ فَأَسۡرِ بِأَهۡلِكَ بِقِطۡعٖ مِّنَ
ٱلَّيۡلِ وَلَا يَلۡتَفِتۡ مِنكُمۡ أَحَدٌ إِلَّا ٱمۡرَأَتَكَۖ إِنَّهُۥ مُصِيبُهَا مَآ أَصَابَهُمۡۚ إِنَّ مَوۡعِدَهُمُ ٱلصُّبۡحُۚ
أَلَيۡسَ ٱلصُّبۡحُ بِقَرِيبٖ ﴿٨١﴾ فَلَمَّا جَآءَ أَمۡرُنَا جَعَلۡنَا عَٰلِيَهَا سَافِلَهَا وَأَمۡطَرۡنَا عَلَيۡهَا حِجَارَةٗ
مِّن سِجِّيلٖ مَّنضُودٖ ﴿٨٢﴾ مُّسَوَّمَةً عِندَ رَبِّكَۖ وَمَا هِيَ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ بِبَعِيدٖ ﴿٨٣﴾

**77-83.** መልዕክተኞቻችን ወደ ሉጥ በመጡ ጊዜ በእነርሱ ምክንያት አዘነ። ልቡም በእነርሱ ተጨነቀ። ይህ ብርቱ ቀን ነውም አለ። ህዝቦቹም ወደ እርሱ እየተጣደፉ መጡና ከዚህም በፊት መጥፎ ሥራዎችን ይሠሩ ነበር። ህዝቦቼ ሆይ፣ እነዚህ ሴቶች ልጆቼ ናቸው። እነሱ ለእናንተ ይልቅ በጣም የፀዱ ናቸው። አግቧቸው እናም አላህን ፍሩ። በእንግዶቼም አታሳፍሩኝ ከናንተ ውስጥ አንድ ቅን ሰው እንኳን የለምን? አላቸው። ከሴቶች ልጆች እኛ ምንም ጉዳይ የለንም። አንተም የምንሻውን በእርግጥ ታውቃለህ አሉት። በእናንተ ላይ ኃይል በኖረኝ ወይም ወደ ብርቱ ወገን ብጠጋ ኖሮ የምሠራውን በሠራሁ ነበር አላቸው። ነብዩ ሉጥ ሆይ! እኛ የጌታህ መልዕክተኞች ነን። ህዝቦች ወደ አንተ በክፉ አይደርሱብህም። ቤተሰብህንም ይዘህ ከሌሊቱ በከፊሉ ውስጥ ሂድ። ከናንተም አንድም ወደ ኋላው አይገላመጥ። ሚስትህ ብቻ ስትቀር። እነሆ እርሷንማ እነርሱን የሚያገኛቸው ስቃይ ሁሉ ያገኛታልና። ቀጠሯቸው ንጋቱ ላይ ነው። ንጋቱ ቅርብ አይደለምን? አሉት። እናም ትዕዛዛችን በመጣ ጊዜ ከተማይቱን ላይዋን ከታችዋ አደረግን ገለበጥናት። ተከታታይም የሆነን የሸክላ ድንጋይ በእርሷ ላይ አዘነብንባት። ከጌታህ ዘንድ ምልክት የተደረገባት ስትሆን አዘነብናት እርሷም ይህች መንደር ከበደለኞቹ ሩቅ አይደለችም።

*وَإِلَىٰ مَدۡيَنَ أَخَاهُمۡ شُعَيۡبٗاۚ قَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥۖ وَلَا تَنقُصُواْ
ٱلۡمِكۡيَالَ وَٱلۡمِيزَانَۖ إِنِّيٓ أَرَىٰكُم بِخَيۡرٖ وَإِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٖ مُّحِيطٖ ﴿٨٤﴾ وَيَٰقَوۡمِ
أَوۡفُواْ ٱلۡمِكۡيَالَ وَٱلۡمِيزَانَ بِٱلۡقِسۡطِۖ وَلَا تَبۡخَسُواْ ٱلنَّاسَ أَشۡيَآءَهُمۡ وَلَا تَعۡثَوۡاْ فِي ٱلۡأَرۡضِ

مُفۡسِدِينَ ﴿٨٥﴾ بَقِيَّتُ ٱللَّهِ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُم مُّؤۡمِنِينَۚ وَمَآ أَنَا۠ عَلَيۡكُم بِحَفِيظٖ ﴿٨٦﴾ قَالُواْ
يَٰشُعَيۡبُ أَصَلَوٰتُكَ تَأۡمُرُكَ أَن نَّتۡرُكَ مَا يَعۡبُدُ ءَابَآؤُنَآ أَوۡ أَن نَّفۡعَلَ فِيٓ أَمۡوَٰلِنَا مَا نَشَٰٓؤُاْۖ
إِنَّكَ لَأَنتَ ٱلۡحَلِيمُ ٱلرَّشِيدُ ﴿٨٧﴾ قَالَ يَٰقَوۡمِ أَرَءَيۡتُمۡ إِن كُنتُ عَلَىٰ بَيِّنَةٖ مِّن رَّبِّي وَرَزَقَنِي
مِنۡهُ رِزۡقًا حَسَنٗاۚ وَمَآ أُرِيدُ أَنۡ أُخَالِفَكُمۡ إِلَىٰ مَآ أَنۡهَىٰكُمۡ عَنۡهُۚ إِنۡ أُرِيدُ إِلَّا ٱلۡإِصۡلَٰحَ
مَا ٱسۡتَطَعۡتُۚ وَمَا تَوۡفِيقِيٓ إِلَّا بِٱللَّهِۚ عَلَيۡهِ تَوَكَّلۡتُ وَإِلَيۡهِ أُنِيبُ ﴿٨٨﴾ وَيَٰقَوۡمِ لَا يَجۡرِمَنَّكُمۡ
شِقَاقِيٓ أَن يُصِيبَكُم مِّثۡلُ مَآ أَصَابَ قَوۡمَ نُوحٍ أَوۡ قَوۡمَ هُودٍ أَوۡ قَوۡمَ صَٰلِحٖۚ وَمَا قَوۡمُ لُوطٖ
مِّنكُم بِبَعِيدٖ ﴿٨٩﴾ وَٱسۡتَغۡفِرُواْ رَبَّكُمۡ ثُمَّ تُوبُوٓاْ إِلَيۡهِۚ إِنَّ رَبِّي رَحِيمٞ وَدُودٞ ﴿٩٠﴾

**84-90.** ወደ መድየን ወንድማቸውን ሹዐይብን ላክን። አላቸው ህዝቦቼ ሆይ፣ አላህን ተገዙ። ከእሱ ሌላ ለእናንተ አምላክ የላችሁም። ስፍርንና ሚዛንን አታጉድሉ። እኔ በፀጋ ላይ ሆናችሁ አያችኋለሁ። እኔም በእናንተ ላይ የከባቢን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ። ህዝቦቼ ሆይ፣ ስፍርንና ሚዛንን በትክክል ሙሉ። ሰዎችን መብቶቻቸውን አታጓድሉባቸው። በምድርም ውስጥ አጥፊዎች ሆናችሁ አታበላሹ። አላህ ያስቀረላችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው። ትክክለኛ ምዕመናን እንደ ሆናችሁ አላህ በሰጣችሁ ውደዱ እኔም መካሪ እንጂ በእናንተ ላይ ተጠባባቂ አይደለሁም። ሹዐይብ ሆይ፣ ስግደትህ አባቶቻችን የሚገዙትን ጣኦታት እንድንተው ወይም በገንዘቦቻችን የምንሻውን መሥራትን (እንድንተው) ታዝሃለችን? አንተ በእርግጥ ታጋሹ ቅኑው አንተ ነህና አሉት። ህዝቦቼ ሆይ!፣ ንገሩኝ እስቲ ከጌታዬ በሆነ አስረጅ ላይ ብሆንና ከእርሱም የሆነን መልካም ሲሳይ ቢሰጠኝ በቅጥፈት ልቀላቅለው ይገባልን? ከርሱ የከለከልኋችሁንም ነገር በመፈፀም ልለያችሁ አልሻም። በተቻለኝ ያህል ማበጀትን እንጂ አልሻም። ለደግ ሥራ መታደሌ በአላህ ፈቃድ ብቻ እንጂ በሌላ አይደለም። በእርሱ ላይ ብቻ ተመካሁ። ወደ እርሱም እመለሳለሁ አላቸው። ወገኖቼ ሆይ እኔን መከራከራችሁ የእነዚህን ህዝቦች ወይም የሁድን ህዝቦች ወይም የሷሊህን ህዝቦች ያገኛቸው ቅጣት ብጤ አይነት እንዲያገኛችሁ አይገፋፋችሁ። የሉጥም ህዝቦች ከናንተ ሩቅ አይደሉም። ጌታችሁን ምህረት ለምኑት ከዚያ ወደ እርሱ ተመለሱ። ጌታዬ አዛኝ፣ ወዳድ ነውና (አላቸው)።

قَالُواْ يَٰشُعَيۡبُ مَا نَفۡقَهُ كَثِيرٗا مِّمَّا تَقُولُ وَإِنَّا لَنَرَىٰكَ فِينَا ضَعِيفٗاۖ وَلَوۡلَا رَهۡطُكَ لَرَجَمۡنَٰكَۖ
وَمَآ أَنتَ عَلَيۡنَا بِعَزِيزٖ ﴿٩١﴾ قَالَ يَٰقَوۡمِ أَرَهۡطِيٓ أَعَزُّ عَلَيۡكُم مِّنَ ٱللَّهِ وَٱتَّخَذۡتُمُوهُ وَرَآءَكُمۡ
ظِهۡرِيًّاۖ إِنَّ رَبِّي بِمَا تَعۡمَلُونَ مُحِيطٞ ﴿٩٢﴾ وَيَٰقَوۡمِ ٱعۡمَلُواْ عَلَىٰ مَكَانَتِكُمۡ إِنِّي عَٰمِلٞۖ سَوۡفَ
تَعۡلَمُونَ مَن يَأۡتِيهِ عَذَابٞ يُخۡزِيهِ وَمَنۡ هُوَ كَٰذِبٞۖ وَٱرۡتَقِبُوٓاْ إِنِّي مَعَكُمۡ رَقِيبٞ ﴿٩٣﴾ وَلَمَّا جَآءَ
أَمۡرُنَا نَجَّيۡنَا شُعَيۡبٗا وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَعَهُۥ بِرَحۡمَةٖ مِّنَّا وَأَخَذَتِ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ ٱلصَّيۡحَةُ فَأَصۡبَحُواْ
فِي دِيَٰرِهِمۡ جَٰثِمِينَ ﴿٩٤﴾ كَأَن لَّمۡ يَغۡنَوۡاْ فِيهَآۗ أَلَا بُعۡدٗا لِّمَدۡيَنَ كَمَا بَعِدَتۡ ثَمُودُ ﴿٩٥﴾

**91-95.** ሹዐይብ ሆይ፣ ከምትለው ነገር ብዙውን አናውቀውም (አይገባንም)። እኛ አንተን በኛ ውስጥ ደከማ ሆነህ እናይሃለን ጎሶችህም ባልኖሩ ኖሮ በወገርንህ ነበር። አንተም በእኛ ላይ የተከበርክ አይደለህም አሉት። ህዝቦቼ ሆይ? ጎሳዎቼ በእናንተ ላይ ከአላህ ይልቅ የከበሩ ናቸውን? አላህን ከኋላችሁ ወደ ጀርባ አድርጋችሁም ያዛችሁት ጌታዬ በምትሠሩት ሁሉ ከባቢ ነው አላቸው። ህዝቦቼም ሆይ!፣ በችሎታችሁ ልክ ሥሩ እኔ ሠሪ ነኝና የሚያዋርደው ቅጣት የሚመጣበትንና እርሱ ውሸታም የሆነው ማን እንደ ሆነ ወደ ፊት ታውቃላችሁ። ጠብቁም እኔ ከናንተ ጋር ተጠባባቂ ነኝና አላቸው። ትዕዛዛችን በመጣ ጊዜ ሹዐይብንና እነዚያን ከእርሱ ጋር ያመኑትን ከእኛ በሆነው ችሮታ አዳን። እነዚያን የበደሉትንም (የጂብሪል) ጩኸት ያዘቻቸው በየቤቶቻቸውም ውስጥ ተንከፍርረው አደሩ። በእርሷ ውስጥ እንዳልነበሩ ሆኑ። (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተዉሉ። ሠሙድ ከአላህ እዝነት እንደራቀች መድየንም ትራቅ።

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (69-95) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙዕሚኖችን ዘወትር በጥሩ ነገር ማብሰር ያለውን ምንዳ፤
2. ሙስሊም ሌላውን ሙስሊም ወንድሙን ባገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሰላምታ ሊያቀርብለት እንደሚገባ፤
3. እንግዳን ተቀብሎ በክብር ማስተናገድ እንግዳው የመጣበት ቤተሰብ አባላት በሙሉ የተጣለባቸው ግዴታ ስለ መሆኑ፤
4. ሚስት በቤተሰብ ውስጥ ትልቅ ቦታ ያላት መሆኗ፤
5. የኢብራሂም ቤተሰብ ከአላህ ክብር የተሰጠውና በእምነት የታነፀ ቤተሰብ እንደሆነ፤
6. ተስፋ የሚጣልበትና ኃላፊነት የሚሰማውን ሰው ማማከር ከእርሱም ጋር መወያየት ተገቢ ስለመሆኑ፤
7. የትዕግስት ምንዳ ትልቅና ሰፊ ስለመሆኑ፤
8. ወደ አላህ ንሰሃ በመግባት ይቅርታን መጠየቅ ምህረትን ብቻ ሳይሆን ተጨማሪ ምንዳን እንደሚያስገኝ፤
9. ስለ የኢብራሂም ሶስት ድንቅ ባህሪያት

10. የተወገዙና የማይገቡ አስቀያሚ ሥነ ምግባሮች ሊያስከትሉ የሚችሉት ውርደትና ኪሣራ እጅግ የከፋ ስለ መሆኑ፤
11. አንድ ችግር የባሰ አደጋ ከማድረሱ በፊት በእንጭጩ መቅጨትና ከተቻለም ችግሩ እንዳይከሰት መከላከል እንደሚገባ፤
12. ወደ መልካም የሚጣራ በጥሩ የሚያዝና ከመጥፎ ተግባር የሚከለክል አስተማሪ በሌለበት ማህበረሰብ ውስጥ መኖር እጅጉን መጥፎ መሆኑን፤
13. መጥፎ ተግባራትን ለማውገዝና የሚያስከትሉትን አደጋ ለመከላከል እንደሁኔታው ኃይልን መጠቀም ተገቢ እንደሆነ፤
14. በሌሊት የሚደረግ ጉዞ በጊዜ ለመድረስና ድካምን ለማስወገድ የሚያስችል በመሆኑ ተፈላጊ መሆኑን፤
15. ከሓዲያን በሚደርሱባቸው ጉዳቶች እንዲሁም የሞት አደጋዎች ምክንያት በሀዘን መዋጥ ትካዜን ማንፀባረቅ ተገቢ አለመሆኑን፤
16. አላህ ኃያል የሆነ ጌታ መሆኑን በርሱ ቁጣ የጠፉትን ከተሞችና ሕዝቦች ታሪክ በመመልከት ማረጋገጥ እንደሚችል፤
17. በግብይት ወቅት በሚዛን ማጉደልና ማጭበርበር ከፍተኛ ወንጀል ስለመሆኑ፤
18. የገቢ መጠን አነስተኛ ቢሆንም በተፈቀዱ ነገሮች መብቃቃት ተገቢ ስለመሆኑ፤
19. የሰዎችን ሐቅ አለመስጠት ወይም መካድ እነርሱን ከመዝረፍ ተለይቶ የማይታይ ወንጀል ስለመሆኑ፤
20. በመሬት ላይ መጥፎ ባህሪያትና ብልሹ ሥነ ምግባሮችን ማስፋፋት የከፋ ወንጀል መሆኑን፤
21. ኢስላማዊ ድንጋጌዎችን በመከተል ኢስላም የሚከለክላቸውን መከልከል የሚያዛቸውን መፈፀም ግዴታ ስለመሆኑ፤
22. ሐቅን ለመቀበል ከማይፈልግ ሰው ጋር አላስፈላጊ ጭቅጭቅ ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን፤
23. ኃጢያትን አምኖ ከወንጀል ታቅቦ ወደ አላህ መመለስና ንስሃ መግባት (ተውበት ማድረግ) ግዴታ ስለመሆኑ፤
24. አላህ እጅግ በጣም አዛኝ ውዴታም የተላበሰ ጌታ መሆኑን ራሱ መግለፁን እንማራለን።

وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَـٰتِنَا وَسُلْطَـٰنٍ مُّبِينٍ ﴿٩٦﴾ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ وَمَلَإِيْهِۦ فَٱتَّبَعُوٓاْ أَمْرَ فِرْعَوْنَ
وَمَآ أَمْرُ فِرْعَوْنَ بِرَشِيدٍ ﴿٩٧﴾ يَقْدُمُ قَوْمَهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ فَأَوْرَدَهُمُ ٱلنَّارَ وَبِئْسَ ٱلْوِرْدُ
ٱلْمَوْرُودُ ﴿٩٨﴾ وَأُتْبِعُواْ فِى هَـٰذِهِۦ لَعْنَةً وَيَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ بِئْسَ ٱلرِّفْدُ ٱلْمَرْفُودُ ﴿٩٩﴾

**96-99.** ሙሳን በታምራቶቻችንና በግልጽ ብርሃን በእርግጥ ላክነው። ወደ ፈርኦንና ወደ ሰዎቹ ላክነው። የፈርኦንን ነገር ህዝቦቹ ተከተሉ። የፈርኦን ነገር ቀጥተኛ አልነበረም። በትንሳኤ ቀን ህዝቦቹን ይቀድማል። ወደ እሳት ያወርዳቸዋል። የሚገቡትም አገባብ ምንኛ ከፋ። በዚችም በቅርቢቱ ዓለም እርግማንን አስከተልናቸው። በትንሳኤም ቀን እንደዚሁ የተሰጡት ስጦታ ምንኛ ከፋ!

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (96-99) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. የአላህ መልካም ፍቃድ ካልታከለበት በስተቀር ማንም ሰው የአላህን ተአምራት ብቻ በመመልከት ወደ እምነት መግባት የማይችል ስለ መሆኑ፤
2. የአላህ ቅጣት ካገኛቸው ሰዎች በሙሉ እጥፍ ድርብ ቅጣት ደርሶባቸዋል ተብለው የሚጠቀሱት በዱንያም ሆነ በአኼራ የአላህ ቅጣት የሚከናነቡ ወንጀለኞች መሆናቸውን እንማራለን።

ቡኻሪና ሙስሊም አቡ ሙሳ አል አሽዐሪን ዋቢ አድርገው በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) «አላህ ለግፈኛ ጊዜ ይሰጠዋል። በያዘው ጊዜ ግን አያመልጠውም።» አሉና (የጌታህ ቅጣት የከተሞችን ሰዎች እነሱ በዳዮች ሲሆኑ በቀጣቸው ጊዜ ልክ እንደሆነ ነው። ቅጣቱ በእርግጥ አሳማሚና ብርቱ ነው።) የሚለውን አነበቡ ብለዋል።

ذَٰلِكَ مِنۡ أَنۢبَآءِ ٱلۡقُرَىٰ نَقُصُّهُۥ عَلَيۡكَۖ مِنۡهَا قَآئِمٞ وَحَصِيدٞ ﴿١٠٠﴾ وَمَا ظَلَمۡنَٰهُمۡ وَلَٰكِن
ظَلَمُوٓاْ أَنفُسَهُمۡۖ فَمَآ أَغۡنَتۡ عَنۡهُمۡ ءَالِهَتُهُمُ ٱلَّتِي يَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مِن شَيۡءٖ لَّمَّا جَآءَ
أَمۡرُ رَبِّكَۖ وَمَا زَادُوهُمۡ غَيۡرَ تَتۡبِيبٖ ﴿١٠١﴾ وَكَذَٰلِكَ أَخۡذُ رَبِّكَ إِذَآ أَخَذَ ٱلۡقُرَىٰ وَهِيَ ظَٰلِمَةٌۚ
إِنَّ أَخۡذَهُۥٓ أَلِيمٞ شَدِيدٌ ﴿١٠٢﴾

**100-102.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ ከላይ የተነገረው ከከተሞቹ ወሬዎች የተወሰነው ነው። በአንተ ላይ እንተርከዋለን። ከእርሷ ቋሚና እጭድም የሆነ አለ። እኛም አልበደልናቸውም። ግን ነፍሶቻቸውን በደሉ። የአላህ ትዕዛዝ በመጣ ጊዜ እነዚያ ከአላህ ሌላ የሚገዙዋቸው አማልክቶቻቸው ሁሉ በምንም አላዳኑዋቸውም። ከማክሰርም በቀር ምንም አልጨመሩላቸውም። የጌታህ ቅጣት የከተሞችን ሰዎች እነሱ በዳዮች ሲሆኑ በቀጣቸው ጊዜ ልክ እንደዚህ ነው። ቅጣቱ በእርግጥ አሳማሚና ብርቱ* ነው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሙሳ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አላህ ለአንድ በደለኛ ሰው የፈለገውን ይሰጠዋል፦ »ሁድ (102) የሚለውን አንቀፅ አነበቡ።

إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّمَنۡ خَافَ عَذَابَ ٱلۡأٓخِرَةِۚ ذَٰلِكَ يَوۡمٞ مَّجۡمُوعٞ لَّهُ ٱلنَّاسُ وَذَٰلِكَ يَوۡمٞ
مَّشۡهُودٞ ﴿١٠٣﴾ وَمَا نُؤَخِّرُهُۥٓ إِلَّا لِأَجَلٖ مَّعۡدُودٖ ﴿١٠٤﴾ يَوۡمَ يَأۡتِ لَا تَكَلَّمُ نَفۡسٌ إِلَّا بِإِذۡنِهِۦۚ
فَمِنۡهُمۡ شَقِيّٞ وَسَعِيدٞ ﴿١٠٥﴾ فَأَمَّا ٱلَّذِينَ شَقُواْ فَفِي ٱلنَّارِ لَهُمۡ فِيهَا زَفِيرٞ وَشَهِيقٌ ﴿١٠٦﴾ خَٰلِدِينَ
فِيهَا مَا دَامَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ إِلَّا مَا شَآءَ رَبُّكَۚ إِنَّ رَبَّكَ فَعَّالٞ لِّمَا يُرِيدُ ﴿١٠٧﴾

**103-107.** በዚህ ውስጥ የመጨረሻውን ቀን ቅጣት ለሚፈሩ ሁሉ መገሰጫ አለ። ይህ የትንሳኤ ቀን ሰዎች በእርሱ የሚሰበሰቡበት ቀን ነው። ይህ የሚጣዱት

ቀን ነው። (ይህንን ቀን) ለተቆጠረም (ለተወሰነ) ጊዜ እንጂ አናቆየውም። በሚመጣ ቀን ማንኛዋም በእርሱ ፈቃድ ቢሆን እንጂ አትናገርም። ከእነርሱ መናጢና (እድለቢስ) እድለኛም አለ። እነዚያ ያመፁትማ በእሳት ውስጥ ናቸው። ለእነርሱ በእርሷ ውስጥ ማናፋትና መንሰቅሰቅ ብቻ አላቸው። ጌታህ ከፈለገው (ጭማሪ) ሌላ ሰማያትና ምድር እስከዘወተሩ* ድረስ በውስጧ ዘውታሪዎች ሲሆኑ (በእሳት ውስጥ ይኖራሉ)። ጌታህ የሚፈልገውን ሠሪ ነውና።

* ይህ አባባል ለዝንተ ዓለም በገሀነም ይኖራሉ ለማለት ነው። ምክንያቱም እዚህ አንቀፅ ላይ ሰማይና ምድር የተባሉት የአኼራዎች ሰማይና ምድር ማለት ነውና።

۞وَأَمَّا ٱلَّذِينَ سُعِدُواْ فَفِي ٱلۡجَنَّةِ خَٰلِدِينَ فِيهَا مَا دَامَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلۡأَرۡضُ إِلَّا مَا شَآءَ رَبُّكَۖ عَطَآءً غَيۡرَ مَجۡذُوذٖ ﴿١٠٨﴾

**108.** እነዚያ እድለኞቹማ* ጌታ ከሻው (ጭማሪ) ሌላ ሰማያትና ምድር እስከ ዘወተሩ ድረስ በውስጧ ዘውታሪዎች ሆነው በገነት ውስጥ ይኖራሉ። የማያቋርጥ ስጦታን ተሰጡ።

* እድለኞችማ...እድለኛ የሚለው ቃል ደስተኛ የተመቸው ማለት ሆኖ በዚህ ቦታ ብዙ ትርጉሞች የተሰጡት ቢሆንም ትክክለኛ እድለኝነት ማለት መልካምን ሰርቶ፤ ለአኼራ ተዘጋጅቶ፤ አዕምሮውን አረጋግቶ፤ ውስጡን አፅድቶ፤ ጧት ማታ ትኩረቱን ወደ ጌታው ያደረገ፤ እጁን የዘረጋ፤ ከፈጣሪም ሆነ ከፍጡር ሐቅ የሚጠነቀቅ፤ በዱንያ ላይ ለሚደረጉት ተጋድሎዎች ከንብረቱ አልፎ ህይወቱን ለመሰዋት ተዘጋጅቶ የሚጠባበቅ፤ ሞት በድንገት እንደሚመጣ በመረዳት ሁልጊዜ የሚጠባበቅ ሰው ነው። እውነትም ደስተኛ ማለት ይህ ነው እንጂ በቁጥር የማይዘለቅ ሀብት ማካበት አይደለም። ዝናው ከሀገር እስከ ሀገር የተዳረሰም አይደለም። በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ሚና ያለውም አይደለም። የፈለገውን መስራት የሚያስችል ድንበር ዘለል የሆነ ስልጣን ያለውም አይደለም። ይህ አንቀፅ "እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉና ከዚያም ቀጥ ያሉ አትፍሩ አትዘኑም በዚያ ተስፋ ቃል ትደረግላችሁ በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ በማለት በእነሱ ላይ መላእክት ይወርዳሉ። ፉሲለት (እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉና ከዚያም ቀጥ ያሉ በእነርሱ ላይ ፍርሃት የለባቸውም እነሱም አያዝኑም።) እነዚያ የገነት ጓዶች ናቸው። በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ሲሆኑ በዚያ ይሠሩት በነበሩት ምክንያት ታላቅን ምንዳ (ይመነዳሉ)። (አህቃፍ፡ **13-14**) እንዳለው ነው።

فَلَا تَكُ فِي مِرۡيَةٖ مِّمَّا يَعۡبُدُ هَٰٓؤُلَآءِۚ مَا يَعۡبُدُونَ إِلَّا كَمَا يَعۡبُدُ ءَابَآؤُهُم مِّن قَبۡلُۚ وَإِنَّا لَمُوَفُّوهُمۡ نَصِيبَهُمۡ غَيۡرَ مَنقُوصٖ ﴿١٠٩﴾ وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَى ٱلۡكِتَٰبَ فَٱخۡتُلِفَ فِيهِۚ وَلَوۡلَا كَلِمَةٞ سَبَقَتۡ مِن رَّبِّكَ لَقُضِيَ بَيۡنَهُمۡۚ وَإِنَّهُمۡ لَفِي شَكّٖ مِّنۡهُ مُرِيبٖ ﴿١١٠﴾ وَإِنَّ كُلّٗا لَّمَّا لَيُوَفِّيَنَّهُمۡ رَبُّكَ أَعۡمَٰلَهُمۡۚ إِنَّهُۥ بِمَا يَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ﴿١١١﴾

**109-111.** እነዚያ ከሓዲያን ከሚገዙት ጣኦት በመጠራጠር ውስጥ አትሁን። አባቶቻቸው ከዚህ በፊት እንደሚገዙት እንጂ አይገዙም። እኛም እነዚህን ፈንታቸውን የማይጓደል ሲሆን የምንሞላላቸው ነን። ለሙሳ መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው። በእርሱም ተለያዩበት ከጌታህ ያለፈች ቃል ባልነበረች ኖሮ በመካከላቸው አሁን ይፈረድ ነበር። እነርሱም ከእርሱ ከቁርኣን አወላዋይ በሆነ መጠራጠር ውስጥ ናቸው። ሁሉንም ጌታህ ሥራዎቻቸውን ምንዳቸውን በእርግጥ ይሞላላቸዋል። እርሱ በሚሠሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና።

فَٱسۡتَقِمۡ كَمَآ أُمِرۡتَ وَمَن تَابَ مَعَكَ وَلَا تَطۡغَوۡاْۚ إِنَّهُۥ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ١١٢

**112.** እንደታዘዝከው ቀጥ በል። ከአንተ ጋር ያመኑትም ቀጥ ይበሉ ወሰንንም አትለፉ እርሱ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

وَلَا تَرۡكَنُوٓاْ إِلَى ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ فَتَمَسَّكُمُ ٱلنَّارُ
وَمَا لَكُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ مِنۡ أَوۡلِيَآءَ ثُمَّ لَا تُنصَرُونَ ١١٣

**113.** ወደ እነዚያም ወደ በደሉት ህዝቦች አትዘንበሉ። እሳት ትነካችኋለችና። ከአላህ ሌላ ጠባቂዎች የሏችሁም ከዚያ አትረዱም።*

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓሲም እንዳስተላለፉት«ለአነስ ነብዩ (ﷺ) «የመዲና ከተማ ክልክል አድርገዋታልን?» ስል ጠየኳቸው። እሳቸውም «አዎን! ከዚህ እስከዚህ ቦታ ድረስ ክልከል አድርገዋል። በርሷ ውስጥ ያለ ዛፍ አይቆረጥም። በርሷ ውስጥ ሆኖ ፈጠራ ወሬ ያወራ የአላህ የመላዕክትና የሰው ልጆች ባጠቃላይ እርግማን በርሱ ላይ ይሁን።»

وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ طَرَفَيِ ٱلنَّهَارِ وَزُلَفٗا مِّنَ ٱلَّيۡلِۚ إِنَّ ٱلۡحَسَنَٰتِ يُذۡهِبۡنَ ٱلسَّيِّـَٔاتِۚ ذَٰلِكَ ذِكۡرَىٰ
لِلذَّٰكِرِينَ ١١٤ وَٱصۡبِرۡ فَإِنَّ ٱللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجۡرَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١١٥

**114-115.** ሶላትንም በቀን ጫፎች ከሌሊትም ክፍሎች ፈጽም። መልካም ሥራዎች ኃጢአቶችን ያስወግዳሉና።*1 ይህ ለተገሳጮች ሁሉ*2 ግሳጼ ነው። ታገስ አላህ የበጎ ሠሪዎችን ምንዳ አያጠፋምና።

*1 ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) «ከናንተ በአንዳችሁ በር ወንዝ የሚያልፍ ቢሆንና ከዚያ ወንዝ በቀን አምስት ጊዜ ቢታጠብ ከአካሉ ላይ ቆሻሻ ይኖርበታል ብላችሁ ታስባላችሁን?»በማለት ባልደረቦቻቸውን ጠየቀ። «የለም፤ ከአካል ላይ ምንም ቆሻሻ አይኖርበትም» ሲሉ መለሱላቸው። እሳቸውም፤ «የአምስት ወቅት ሶላቶች ምሳሌም እንደዚሁ ነው። አላህ በነርሱ አማካኝነት ወንጀሎችን ያብሳል» አሉ።

ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላለፉት አንድ ሰው አንዲትን ባዕድ ሴት ሳመ። ከነብዩ ዘንድ መጣና የፈፀመውን ስህተት ነገራቸው። አላህም ይህን አንቀፅ አወረደ፡- መስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አምስት ወቅት ሶላቶችና ከጁመዓ እስከ ጁመዓ ያሉት ጊዜያት በመካከላቸው የተፈፀሙ ኃጢአቶችን የሚያሳምሩ ናቸው። ይህ የሚሆነው ታላለቅ ወንጀሎች እስካልተፈፀሙ ድረስ ነው።»

✷2 ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላፉት ቲርሚዚይ በዘገቡት ሐዲስ አንድ ሰው አንዲትን ሴት ስሞ በመፀፀት ወደ አላህ መልዕክተኛ መጣና ሁኔታውን ሁሉ ነገራቸው። በዚህም ምክኒያት የሚከተለው የቁርአን አንቀፅ ወረደ «ሶላትንም በቀን ጫፎች ጠዋትና ከቀትር በኋላ ከሌሊትም ክፍሎች ፈፅም፤ መልካም ስራዎች ኃጢአቶችን ያስወግዳሉና፤ ይህ ለተገሳጮች ግሳጼ ነው» (ሁድ፡ **114**) ሰውየውም «ይህ ለኔ ነውን?» ሲል ጠየቀ። እሳቸውም «ከኔ ሕዝቦች መካከል ለሚተገብሯት ሁሉ ነው» አሉት። (ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡበክር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ አሉኝ፡- «የትም ብትሆን አላህን ፍራ፤ መጥፎ ስራ ከሰራህ መልካምን አስከትል። መልካም ስራ መጥፎዋን ስራ ታስወግዳለች። ሰዎችንም በመልካም ሥነ. ምግባር ተቀላቀለቸው።»

ከሁድ ምዕራፍ (**114**) ኛ አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩ (ﷺ) ዘመን አንድ ሰው ወደ እሳቸው በመምጣት «በመዲና ከተማ ጠረፍ ላይ እየነገድኩ ሳለ አንዲት ባልዋ ዘመቻ የሄደባት ሴት ተምር እንድሸጥላት ጠይቀችኝ ስላማረችኝ ከዚህ ተምር የተሻለ ከቤቴ አለ በማለት ተከተይኝ ብዬ ወደቤቴ ከወሰድኳት በኋላ ባል በሚስቱ ላይ ሊያደርገው የሚችለውን ነገር ሁሉ ከግብረ ሥጋ ግንኙነት በስተቀር አደረኩኝ። ከሄደች በኋላ በድርጊቱ ተፀፅቼ ወደ ዑመር ሄጄ ታሪኬን ስነግራቸው ወየውልህ ባሏ ጂሀድ የሄደ እንዳይሆን አሉኝ። አዎን በማለት ስመልስላቸው ወደ አቡበከር ሂድና መፍትሄ ሞክር አሉኝ። ወደ አቡበከርም ሂጄ ስጠይቅ ተመሳሳይ መልስ ሰጡኝና እስቲ ነብዩን አናግር አሉኝ። ነብዩን (ﷺ) ዘንድ ሂጄ ልክ ዑመርን እንደጠየኩት ጠየኩ። ሁኔታውን ሲረዱ መልስ ከመስጠት ተቆጥተው ፀጥ ብለው ባሉበት ይህ አንቀፅ ወረደና መፍትሔ ሰጠ። ሰውዬም በጣም ተደስቶ ለእኔ ብቻ ናት። ይህች ህግ ወይስ ለሁሉም ትሠራለች አለ። ዑመር ኢብኑል ኸጣብም ልቡን መታ አድርገው ለሁሉ ነው እንጂ ምን ነካህ አንተ ሲሉት ነብዩ (ﷺ) ፈገግ ብለው ዑመር ትክክል ነው የተናገረው አሉ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

فَلَوۡلَا كَانَ مِنَ ٱلۡقُرُونِ مِن قَبۡلِكُمۡ أُوْلُواْ بَقِيَّةٖ يَنۡهَوۡنَ عَنِ ٱلۡفَسَادِ فِي ٱلۡأَرۡضِ إِلَّا قَلِيلٗا
مِّمَّنۡ أَنجَيۡنَا مِنۡهُمۡۗ وَٱتَّبَعَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ مَآ أُتۡرِفُواْ فِيهِ وَكَانُواْ مُجۡرِمِينَ ١١٦ وَمَا كَانَ رَبُّكَ
لِيُهۡلِكَ ٱلۡقُرَىٰ بِظُلۡمٖ وَأَهۡلُهَا مُصۡلِحُونَ ١١٧ وَلَوۡ شَآءَ رَبُّكَ لَجَعَلَ ٱلنَّاسَ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗۖ
وَلَا يَزَالُونَ مُخۡتَلِفِينَ ١١٨ إِلَّا مَن رَّحِمَ رَبُّكَۚ وَلِذَٰلِكَ خَلَقَهُمۡۗ وَتَمَّتۡ كَلِمَةُ رَبِّكَ لَأَمۡلَأَنَّ
جَهَنَّمَ مِنَ ٱلۡجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ أَجۡمَعِينَ ١١٩

**116-119.** ከናንተ በፊት ከነበሩት ከክፍለ ዘመናት ሰዎች ውስጥ በምድር ላይ ከማበላሸት የሚከለክሉ የመልካም ሥራዎች ቅሬት ባለቤቶች ለምን አልነበሩም ግን ከእነርሱ ያዳንናቸው ጥቂቶቹ (ከለከሉና) ዳኑ። እነዚያም የበደሉት ሰዎች (አልከለከሉም) በእርሱ የተቀማጠሉበትን ተድላ ተከተሉ

አመጸኞችም ነበሩ። ጌታህ ከተሞችን ባለቤቶቻቸው መልካም ሠሪዎች ሆነው ሳሉ በመበደል የሚያጠፋቸው አልነበረም። ጌታህ በሻ ኖሮ ሰዎችን ሁሉ አንድ ህዝብ ባደረጋቸው ነበር የተለያዩም ከመሆን አይወገዱም። ጌታህ ያዘነለት ብቻ ሲቀር (ከመለያየት አይወገዱም)። ለዚሁም ነው የፈጠራቸው። የጌታህ ቃል ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች ከሁሉም በእርግጥ እሞላታለሁ በማለት ተፈፀመች።

وَكُلًّا نَّقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنۢبَآءِ ٱلرُّسُلِ مَا نُثَبِّتُ بِهِۦ فُؤَادَكَۚ وَجَآءَكَ فِي هَٰذِهِ ٱلْحَقُّ وَمَوْعِظَةٌ وَذِكْرَىٰ لِلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٢٠﴾ وَقُل لِّلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ ٱعْمَلُواْ عَلَىٰ مَكَانَتِكُمْ إِنَّا عَٰمِلُونَ ﴿١٢١﴾ وَٱنتَظِرُوٓاْ إِنَّا مُنتَظِرُونَ ﴿١٢٢﴾

**120-122.** ከመልዕክተኞቹ ዜናዎች (ተፈላጊውን) ሁሉንም ልብህን በእርሱ የምናፀናበትን እንተርክልሀለን በዚህችም ሱራ እውነቱ ነገር ለምእምናን ግሳጼና ማስታወሻ መጥቶልሀል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነዚያም ለማያምኑት፡ ባላችሁበት ሁኔታ ላይ ሥሩ። እኛ ሠሪዎች ነንና በላቸው። (ሙሐመድ ሆይ!) የራሳችሁን ውጤት ተጠባበቁ እኛ ተጠባባቂዎች ነንና በላቸው።

وَلِلَّهِ غَيْبُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَإِلَيْهِ يُرْجَعُ ٱلْأَمْرُ كُلُّهُۥ فَٱعْبُدْهُ وَتَوَكَّلْ عَلَيْهِۚ وَمَا رَبُّكَ بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعْمَلُونَ ﴿١٢٣﴾

**123.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሰማያትና በምድር ያለው ሚስጥር ሁሉ የአላህ ነው። ሁሉም ነገር ወደ እርሱ ብቻ ይመለሳል። ስለዚህ እሱን ብቻ ተገዛው። በእርሱም ላይ ብቻ ተመካ። ጌታህም ከሚሰሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም።

**ከሁድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (100-123) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ በምንም አይነት ሰዎችን የማይበድልና ከግፍ የጠራ አምላክ ስለ መሆኑ፤
2. ከሓዲያን የሚያመልኳቸው የሀሰት አማልክት በሙሉ ጥቅምን መስጠትም ሆነ ጉዳትን ማስቀረት የማይችሉ መሆናቸውን፤
3. ግፍን ማራመድና ሰውን መበደል በኢስላም አስቀያሚ ተግባር ስለመሆኑ፤
4. በመጨረሻው ቀን ማመን ክብርንና ትልቅ ደረጃ የሚያጎናፅፍ ስለመሆኑ፤
5. ከሞት በኋላ መቀስቀስ መኖሩ የማይቀር ስለመሆኑ፤
6. የቂያማ ዕለት ማንም ሰው የአላህን ፍቃድ ሳያገኝ ለመናገር እንደማይችል፤

7. የአላህ ችሎታ እጅግ የተሟላ እንከን የማይወጣለት መሆኑን፤
8. አላህ ቢፈልግ የእሳትን ሰዎች ከእሳት ለማውጣትና የጀነት ሰው እንዲሆኑ ለማድረግ የማይሳነው አምላክ ስለ መሆኑ፤
9. ነብዩ (ﷺ) በዳዕዋ ቸው ላይ ተበራትተው እንዲቀጥሉ የአላህ የሞራል ድጋፍ እንዳልተለያቸው፤
10. ወንጀለኞች በሰሩት ኃጢአት በዱንያ ባይቀጡም በሰፊው አኼራ ላይ እንደሚጠብቃቸው፤
11. አላህ የደነገገውን ሕግ መጣስና ድንጋጌውን አለማክበር ክልክል መሆኑን፤
12. ከከሓዲያን ጋር መመሣሰል እጅግ በጣም የተወገዘ ወንጀል ስለመሆኑ፤
13. የአምስት ወቅት ሶላቶችን ወቅቱንና ደንቡን ጠብቆ መስገድ ከዋና ዋና ኢስላማዊ ግዴታዎች መሆኑን፤
14. መልካም ሥራ የመጥፎ ስራንና የኃጢያት ቅጣት የሚያሰርዝ ስለመሆኑ፤
15. ትዕግስትና መልካም ተግባር የኢስላም መገለጫዎች በመሆናቸው እነሱን መላበስ መሽቀዳደም እንደሚገባ፤
16. በመልካም የሚይዙትና ከመጥፎ የሚከለከሉት ዳኢዎች እስካሉ ድረስ ሙስሊሞችና ባጠቃላይ ህብረተሰቡ በመልካም ሁኔታ ለመኖር የሚያስችለው አጋጣሚ መኖሩን፤
17. ምቾት አብዛኛውን ጊዜ ወደ ወንጀል ተግባራት የሚገፋፉ መሆኑን፤
18. ስምምነትና አንድነት የአላህን ርህራሄ የሚያስገኙ የእዝነት በሮች መሆናቸውን፤
19. ጥልና ጭቅጭቅ የአላህን ቁጣ የሚያወርዱ መሆናቸውን፤
20. አላህ በምንም አይነት ሰዎችን የማይበድልና ከግፍ የጠራ አምላክ መሆኑ፤
21. ከሓዲያን የሚያመልኳቸው የሀሰት አማልክት በሙሉ ጥቅምን መስጠትም ሆነ ጉዳትን ማስቀረት የማይችሉ መሆናቸውን፤
22. ግፍን ማራመድና ሰውን መበደል በኢስላም አስቀያሚ ተግባር ስለመሆኑ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የነብዩ ሁድ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (12)
# የነብዩ ዩሱፍ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ዩሱፍ)

سُورَةُ يُوسُفَ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (111) ናቸው።
### የሱረቱ ዩሱፍ መግቢያ

ይህን ስያሜ ያገኘው በዚሁ ምዕራፍ በብዛት ታሪካቸው በተወሱት ነብይ ስም ነው። ይህ ነብይ በቁርኣን ውስጥ ሶስት ጊዜ ተወስቷል።

በእንስሳት ምዕራፍ በ (84) ኛው፤ በዚሁ በዩሱፍ ምዕራፍ በተደጋጋሚ፤ በጋፊር ምዕራፍ አናቅፅ ላይ ነው።

ከመቶ አስራ አንድ አንቀፆቹ ዘጠና ስምንቱ አናቅፅ በዋነኝነት የሚተርኩት ስለ ነብዩ ዩሱፍ ነው። መግቢያ ያደረጋቸው ሶስት አናቅፅ ደግሞ ስለ ቁርኣንና ስለ ነብዩ (ﷺ) ያወሳሉ። በቀሩት አስር አናቅፅ ደግሞ ነብዩ (ﷺ) ስለዚህ ታሪክ ምንም ያውቁ እንዳልነበርና ከነብዩ ዩሱፍ ወንድሞች ጋርም አብረው እንዳልነበሩ በይፋ ይገልፃል።

የእነዚህ ነብያት ታሪክ አዕምሮ ላለው ሰው ሁሉ ከፍተኛ አስተምህሮት እንዳለውም ያብራራል።

የነብዩ ዩሱፍን ታሪክ በሙሉ ይተርካል ባይባልም አብዛኛውን አካቶታል። በተጨማሪ በየዕቁብ ቤተሰቦች ውስጥ ምቀኝነት እንዴት ተንሰራፍቶ እንደነበረና ምቀኝነት ለብዙ አደጋዎች ሊያጋልጥ እንደሚችል ገልፆ አላህ ነብዩ ዩሱፍን ከወንድሞቹ ሴራና አድማ እንደጠበቃቸው ያብራራል።

ይህም ለነብዩ (ﷺ) ከፍተኛ ማጽናኛ እና ማበረታቻ ነበር። የመናምን (የህልምን) ፍቺ አላህ ከመልካም ባሮቹ መካከል ለሚሻው ሰው እንደሚሰጥ በቤተሰብም መካከል ምቀኝነት ሊገባ እንደሚችል ያስገነዝባል።

እዚህ ላይ ቁርኣን በምን ቋንቋ ወረደ? ለሚለው ጥያቄ በቂ መልስ የተሰጠበት ነው፡- «እኛ (ፍችውን) እወቁ።» የዚህን አንቀፅ መልዕክት በተመሳሳይና ብሎም ሰፋ ባለመልኩ የሚገልፁ አናቅፅ ብዙ ናቸው በጥቂቱ እንመልከት። «እንደዚሁ በአረብኛ የተነገረ ፍትህ ሲሆን አወረድነው» (አልረዕድ፡ 37)፡

አረብኛ ቁርኣን ሲሆን ለሚያውቁ ህዝቦች (የተብራራ) ነው።» (ፉሲለት፡ 2)

«እነዚህ እነርሱም እርሱን (ቁርኣንን) የሚያስተምረው ሰው ብቻ ነው ማለታቸውን በእርግጥ እናውቃለን። የዚያ ወደ እርሱ የሚያስጠጉበት ሰው ቋንቋ ዐጀም ነው። ይህ (ቁርኣን) ግን ግልጽ አረብኛ ቋንቋ ነው።» (የጉንዳኗ ምዕራፍ፡ 103)

«እርሱም (ቁርኣን) በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው። እርሱን ታማኙ መንፈስ (ጅብሪል) አወረደው። ግልጽ በሆነ አረብኛ ቋንቋ» (አሸሹዓራእ፡ 192-195) “እንደዚሁም... አረብኛ የሆነን ቁርኣን ወደ አንተ አወረድን» (አሸሹራ፡ 7) «እኛ ታውቁ ዘንድ አረብኛ ቁርኣን አደረግነው።» (አዝዙኽሩፍ፡ 3)

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓرۚ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡمُبِينِ ١ إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ قُرۡءَٰنًا عَرَبِيّٗا لَّعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ٢
نَحۡنُ نَقُصُّ عَلَيۡكَ أَحۡسَنَ ٱلۡقَصَصِ بِمَآ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانَ
وَإِن كُنتَ مِن قَبۡلِهِۦ لَمِنَ ٱلۡغَٰفِلِينَ ٣

**1-3.** አሊፍ፤ ላም፤ ራ፤ (በእነዚህ ፊደሎች ምን እንደፈለገ አላህ ራሱ ብቻ ያውቃል)።*1 እነዚህ አንቀፆች ግልጽና የተብራራ ከሆነው መጽሐፍ አንቀፆች መካከል ከፊሎቹ ናቸው። (ዐረቦች ሆይ)፣ እኛ ቁርኣንን ትረዱት ዘንድ በአረበኛ ቋንቋ አወረድነው።*2 (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ይህንን የቁርኣን ክፍል ወደ አንተ በማውረዳችን እጅግ ውብና ማራኪ የሆነ ታሪክ እንተርክልሃለን። እነሆ ከዚህ በፊት አንተም ይህንን ታሪክ በእርግጥ ከማያውቁት ነበርክ።

✱1 (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፲ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

✱2 የነብዩ (ﷺ) ሱሃባዎች ልዩ ልዩ ትረካ እንዲተረክላቸው ተመኝተው ነብዩን (ﷺ) ሲያናግሯቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

إِذۡ قَالَ يُوسُفُ لِأَبِيهِ يَٰٓأَبَتِ إِنِّي رَأَيۡتُ أَحَدَ عَشَرَ كَوۡكَبٗا وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ رَأَيۡتُهُمۡ لِي
سَٰجِدِينَ ٤ قَالَ يَٰبُنَيَّ لَا تَقۡصُصۡ رُءۡيَاكَ عَلَىٰٓ إِخۡوَتِكَ فَيَكِيدُواْ لَكَ كَيۡدًاۖ إِنَّ ٱلشَّيۡطَٰنَ
لِلۡإِنسَٰنِ عَدُوّٞ مُّبِينٞ ٥ وَكَذَٰلِكَ يَجۡتَبِيكَ رَبُّكَ وَيُعَلِّمُكَ مِن تَأۡوِيلِ ٱلۡأَحَادِيثِ وَيُتِمُّ
نِعۡمَتَهُۥ عَلَيۡكَ وَعَلَىٰٓ ءَالِ يَعۡقُوبَ كَمَآ أَتَمَّهَا عَلَىٰٓ أَبَوَيۡكَ مِن قَبۡلُ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡحَٰقَۚ إِنَّ
رَبَّكَ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ٦

**4-6.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ነብዩ ዩሱፍ በልጅነቱ ለአባቱ አባቴ ሆይ፣ እኔ አስራ አንድ ኮከቦችን፤ ጨረቃንና ፀሐይን ሲሰግዱልኝ በሕልሜ አየሁኝ ባለ ጊዜ የሆነውን ታሪክ ለህዝቦችህ (አስታውስ)። አባቱም ልጄ ሆይ፣ ይህን ህልምህን ለወንድሞችህ አትንገር። በአንተ ላይ ተንኮል እንዳያሴሩ።

ምክንያቱም ሰይጣን ለሰው ልጅ ሁልጊዜም ግልፅ ጠላት ነውና አለ። ጌታህ ልክ ይህን ህልም እንዳሳየህ ሁሉ (ለነብይነትም) ይመርጥሃል። የንግግሮችን ፍች ያስተምርሃል። ፀጋውንም ቀደም ሲል ለአባቶችህ ለኢብራሂምና ለኢስሃቅ እንደሞላ ሁሉ ለአንተና ለያዕቁብ ቤተሰቦችም ይሞላል። ጌታህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና።

۞ لَّقَدْ كَانَ فِي يُوسُفَ وَإِخْوَتِهِۦٓ ءَايَٰتٌ لِّلسَّآئِلِينَ ٧ إِذْ قَالُوا۟ لَيُوسُفُ وَأَخُوهُ أَحَبُّ إِلَىٰٓ
أَبِينَا مِنَّا وَنَحْنُ عُصْبَةٌ إِنَّ أَبَانَا لَفِي ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ٨ ٱقْتُلُوا۟ يُوسُفَ أَوِ ٱطْرَحُوهُ أَرْضًا يَخْلُ
لَكُمْ وَجْهُ أَبِيكُمْ وَتَكُونُوا۟ مِنۢ بَعْدِهِۦ قَوْمًا صَٰلِحِينَ ٩ قَالَ قَآئِلٌ مِّنْهُمْ لَا تَقْتُلُوا۟
يُوسُفَ وَأَلْقُوهُ فِي غَيَٰبَتِ ٱلْجُبِّ يَلْتَقِطْهُ بَعْضُ ٱلسَّيَّارَةِ إِن كُنتُمْ فَٰعِلِينَ ١٠ قَالُوا۟ يَٰٓأَبَانَا
مَا لَكَ لَا تَأْمَ۫نَّا عَلَىٰ يُوسُفَ وَإِنَّا لَهُۥ لَنَٰصِحُونَ ١١ أَرْسِلْهُ مَعَنَا غَدًا يَرْتَعْ وَيَلْعَبْ وَإِنَّا
لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ١٢ قَالَ إِنِّي لَيَحْزُنُنِيٓ أَن تَذْهَبُوا۟ بِهِۦ وَأَخَافُ أَن يَأْكُلَهُ ٱلذِّئْبُ وَأَنتُمْ
عَنْهُ غَٰفِلُونَ ١٣ قَالُوا۟ لَئِنْ أَكَلَهُ ٱلذِّئْبُ وَنَحْنُ عُصْبَةٌ إِنَّآ إِذًا لَّخَٰسِرُونَ ١٤

**7-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዩሱፍና የወንድሞቹ ታሪክ እውቀትን በመሻት ለሚጠይቁ ሁሉ ትምህርት ሰጪ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ በቁጥር ብዙዎች ሁነን እያለ ዩሱፍና ወንድሙ ከአባታችን ዘንድ ከእኛ ይበልጥ ተወዳጆች ናቸው። በእውነቱ አባታችን ግልጽ ስህተት ውስጥ ነው (ባሉ ጊዜ የሆነውን አስታውስ)። ዩሱፍን ግደሉት ወይም እሩቅ ቦታ ጣሉት። ይህን ካረጋችሁ የአባታችሁን ፊት ትኩረትና ውዴታ የራሳችሁ ብቻ ታደርጋላችሁ። ከዚህ በኋላ ከኃጥያታችሁ በመመለስ መልካም ሰዎች ትሆናላችሁ። (ተባባሉ) ከመካከላቸው አንዱ ተናጋሪ ዩሱፍን አትግደሉት። ይልቁንም የምትፈፅሙት ከሆነ የሆኑ መንገደኞች እንዲያነሱት በጉድጓድ ወለል ውስጥ ጣሉት። አባታችን ሆይ፣ በዩሱፍ ጉዳይ እኛ ለእርሱ መልካም ተመኚዎች ሁነን ለምን አታምነንም አሉ። እስቲ ይዝናና ይጫወት ዘንድ ነገ ከእኛ ጋር አብረህ ላከው። እኛ በትክክል አንጠብቀዋለን። (በማለት ጠየቁ)። አባቱም እርሱን መውሰዳችሁ ያሳዝነኛል። ዘንግታችሁት (ችላ ብላችሁት) ተኩላ ይበላዋል ብየ እፈራለሁ አለ። እነርሱም እኛ እንዲህ ቁጥራችን ብዙ ሆኖ ተኩላ ከበላውማ ከሳሪዎች እኛ ነን አሉ።

فَلَمَّا ذَهَبُواْ بِهِۦ وَأَجۡمَعُوٓاْ أَن يَجۡعَلُوهُ فِي غَيَٰبَتِ ٱلۡجُبِّۚ وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡهِ لَتُنَبِّئَنَّهُم بِأَمۡرِهِمۡ هَٰذَا
وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ١٥ وَجَآءُوٓ أَبَاهُمۡ عِشَآءٗ يَبۡكُونَ ١٦ قَالُواْ يَٰٓأَبَانَآ إِنَّا ذَهَبۡنَا نَسۡتَبِقُ
وَتَرَكۡنَا يُوسُفَ عِندَ مَتَٰعِنَا فَأَكَلَهُ ٱلذِّئۡبُۖ وَمَآ أَنتَ بِمُؤۡمِنٖ لَّنَا وَلَوۡ كُنَّا صَٰدِقِينَ ١٧
وَجَآءُو عَلَىٰ قَمِيصِهِۦ بِدَمٖ كَذِبٖۚ قَالَ بَلۡ سَوَّلَتۡ لَكُمۡ أَنفُسُكُمۡ أَمۡرٗاۖ فَصَبۡرٞ جَمِيلٞۖ وَٱللَّهُ
ٱلۡمُسۡتَعَانُ عَلَىٰ مَا تَصِفُونَ ١٨

**15-18.** ወሰደውት በጉድጓድ ወለል ላይ ሊጥሉት በወሰኑ ጊዜ እነርሱ ሳያውቁ ይህን ፀያፍ ተግባራቸውን ወደ ፊት ትነግራቸዋለህ የሚል መልዕክት ላክንለት። አባታቸውንም በምሽት እያለቀሱ መጡለት። አባታችን ሆይ፣ እኛ ለሩጫና ለውርወራ ልንሽቀዳደም ሄድን ዩሱፍንም እቃችን ዘንድ ተውነው። ወዲያውም ተኩላ በላው። አንተንም እውነተኞች ብንኾንም የምታምነን አይደለህም አሉ። በቀሚሱም ላይ የውሸትን ደም አመጡ። አባታቸው ይህ ትክክል አይደለም። ነፍሶቻችሁ ውሸት ነገርን ሸለሙላችሁ። ስለዚህ መልካም ትዕግስት (ማድረግ አለብኝ)። በምትሉትም ነገር ላይ መታገዣው አላህ ብቻ ነው አለ።

وَجَآءَتۡ سَيَّارَةٞ فَأَرۡسَلُواْ وَارِدَهُمۡ فَأَدۡلَىٰ دَلۡوَهُۥۖ قَالَ يَٰبُشۡرَىٰ هَٰذَا غُلَٰمٞۚ وَأَسَرُّوهُ بِضَٰعَةٗۚ وَٱللَّهُ
عَلِيمُۢ بِمَا يَعۡمَلُونَ ١٩ وَشَرَوۡهُ بِثَمَنِۭ بَخۡسٖ دَرَٰهِمَ مَعۡدُودَةٖ وَكَانُواْ فِيهِ مِنَ ٱلزَّٰهِدِينَ ٢٠

**19-20.** መንገደኞችም መጡ። ውሃ ቀጂያቸውን ላኩ። አኮሌውንም ወደ ጉድጓዱ ሰደደ። የምስራች!። ይህ ልጅ ነው አለ። ሸቀጥ አድርገውም ደበቁ። አላህ የሚሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው። በርካሽ ዋጋና በሚቆጠሩ ዲርሃሞች ሸጡት። በእርሱም ላይ ከቸልተኞቹ ነበሩ።

وَقَالَ ٱلَّذِي ٱشۡتَرَىٰهُ مِن مِّصۡرَ لِٱمۡرَأَتِهِۦٓ أَكۡرِمِي مَثۡوَىٰهُ عَسَىٰٓ أَن يَنفَعَنَآ أَوۡ نَتَّخِذَهُۥ وَلَدٗاۚ وَكَذَٰلِكَ
مَكَّنَّا لِيُوسُفَ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلِنُعَلِّمَهُۥ مِن تَأۡوِيلِ ٱلۡأَحَادِيثِۚ وَٱللَّهُ غَالِبٌ عَلَىٰٓ أَمۡرِهِۦ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ
ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٢١ وَلَمَّا بَلَغَ أَشُدَّهُۥٓ ءَاتَيۡنَٰهُ حُكۡمٗا وَعِلۡمٗاۚ وَكَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٢٢

**21-22.** ያም ከግብጽ የገዛው ሰው ለሚስቱ ይህ ልጅ መኖሪያውን አክብሪ ሊጠቅመን ወይም ልጅ አድርገን ልንይዘው ይከጅላልና አላት። እንደዚሁም ለዩሱፍ ገኸ ልናደርገውና የሕልሞችንም ፍች ልናስተምረው በምድር ላይ አስመቸነው። አላህ በሁሉ ነገር ላይ አሸናፊ ነውና። ግን አብዛኞቹ ሰዎች

ይህን አያውቁም። ጥንካሬውንም በደረሰ ጊዜ ጥበብንና ዕውቀትን ሰጠነው። ልክ እንደዚህም መልካም ሠሪዎችን ሁሉ እንመነዳለን።

وَرَٰوَدَتۡهُ ٱلَّتِي هُوَ فِي بَيۡتِهَا عَن نَّفۡسِهِۦ وَغَلَّقَتِ ٱلۡأَبۡوَٰبَ وَقَالَتۡ هَيۡتَ لَكَۚ قَالَ مَعَاذَ ٱللَّهِۖ
إِنَّهُۥ رَبِّيٓ أَحۡسَنَ مَثۡوَايَۖ إِنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٢٣ وَلَقَدۡ هَمَّتۡ بِهِۦۖ وَهَمَّ بِهَا لَوۡلَآ أَن
رَّءَا بُرۡهَٰنَ رَبِّهِۦۚ كَذَٰلِكَ لِنَصۡرِفَ عَنۡهُ ٱلسُّوٓءَ وَٱلۡفَحۡشَآءَۚ إِنَّهُۥ مِنۡ عِبَادِنَا ٱلۡمُخۡلَصِينَ ٢٤
وَٱسۡتَبَقَا ٱلۡبَابَ وَقَدَّتۡ قَمِيصَهُۥ مِن دُبُرٖ وَأَلۡفَيَا سَيِّدَهَا لَدَا ٱلۡبَابِۚ قَالَتۡ مَا جَزَآءُ مَنۡ
أَرَادَ بِأَهۡلِكَ سُوٓءًا إِلَّآ أَن يُسۡجَنَ أَوۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ ٢٥ قَالَ هِيَ رَٰوَدَتۡنِي عَن نَّفۡسِيۚ وَشَهِدَ
شَاهِدٞ مِّنۡ أَهۡلِهَآ إِن كَانَ قَمِيصُهُۥ قُدَّ مِن قُبُلٖ فَصَدَقَتۡ وَهُوَ مِنَ ٱلۡكَٰذِبِينَ ٢٦ وَإِن كَانَ
قَمِيصُهُۥ قُدَّ مِن دُبُرٖ فَكَذَبَتۡ وَهُوَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ٢٧ فَلَمَّا رَءَا قَمِيصَهُۥ قُدَّ مِن دُبُرٖ قَالَ
إِنَّهُۥ مِن كَيۡدِكُنَّۖ إِنَّ كَيۡدَكُنَّ عَظِيمٞ ٢٨ يُوسُفُ أَعۡرِضۡ عَنۡ هَٰذَاۚ وَٱسۡتَغۡفِرِي لِذَنۢبِكِۖ
إِنَّكِ كُنتِ مِنَ ٱلۡخَاطِـِٔينَ ٢٩

**23-29.** ያችም እርሱ በቤትዋ የነበረባት ሴት ከነፍሱ አባበለችው። ደጃፎቹንም ዘጋችና ይኸው ለአንተ ተዘጋጂቼልሃለሁና ቶሎ በል ናም አለችው። እሱም ከዚህ ፀያፍ ተግባር በአላህ እጠበቃለሁ። እርሱ አሳዳሪየ ኑሮዬን ያሳመረልኝ ነውና። አልከዳውም። እነሆ በደለኞች አይድኑምና አላት። በእርሱም በእርግጥ አሰበች። በእርሷም አሰበ። የጌታውን ማስረጃ ባላዬ ኖሮ። (በእርሷም ባሰበ ነበር)። እንደዚሁ መጥፎ ነገርንና ኃጢአትን ከእርሱ ላይ ልንመልስለት (አስረጃችንን አሳየነው)። እርሱ ከተጠበቁት ባሮቻችን አንዱ ነዉና። እርሱና እርሷ በሩን ተሽቀዳደሙና ቀሚሱን ከኋላው ቀደደችው ባለቤትዋን በሩ አጠገብ አገኙት። እሷም ቀደም ብላ በባለቤትህ መጥፎን ያሰበ ሰው ቅጣቱ መታሰር ወይም አሳማሚ ስቃይ እንጂ ሌላ አይደለም አለችው። ዩሱፍም እርሷ ናት ከነፍሴ የአባበለችኝ አለ። ከቤተሰቦቿም አንድ መስካሪ ቀሚሱ ከበስተፊት ተቀዶ ከሆነ እሷ እውነት ተናገረች። እርሱ ከውሸታሞቹ አንዱ ነው በማለት መሰከረ። ቀሚሱም ከበስተኋላው ተቀዶ እንደሆነ ዋሸች። እርሱም ከእውነተኞቹ ነው። ቀሚሱንም ከበስተኋላ ተቀዶ ባየ ጊዜ እርሱ የተናገርሽው ከተንኮላችሁ ነው። የእንናንተ የሴቶች ተንኮል ብርቱ ነውና አላት።* ዩሱፍ ሆይ፣ አንተም ከዚህ ወሬ ተከልከል። አንቺም ለኃጢአትሽ ማርታን ለምኝ። አንቺ ከስሕተተኞቹ ሆነሻልና አለ።

✴ በዚህ አንቀፅ ዙሪያ ብዙ ነገሮች ተወርተዋል። ነብዩ (ﷺ) አህመድ ኢብኑ ጀሪር በይሐቂ በዘገቡት ሐዲስ ሕፃን ሆነው የተናገሩ አራት ናቸው። እነሱም የፈርዖንን ልጅ ፀጉር ሞሻጭ ልጅ፤ የዩሱፍ ምስክር፤ የጁረይጅ ጓደኛና የመርየም ልጅ ዒሳ ናቸው» ብለዋል።

۞وَقَالَ نِسْوَةٌ فِى ٱلْمَدِينَةِ ٱمْرَأَتُ ٱلْعَزِيزِ تُرَٰوِدُ فَتَىٰهَا عَن نَّفْسِهِۦ ۖ قَدْ شَغَفَهَا حُبًّا ۖ إِنَّا
لَنَرَىٰهَا فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٣٠﴾ فَلَمَّا سَمِعَتْ بِمَكْرِهِنَّ أَرْسَلَتْ إِلَيْهِنَّ وَأَعْتَدَتْ لَهُنَّ مُتَّكَـًٔا
وَءَاتَتْ كُلَّ وَٰحِدَةٍ مِّنْهُنَّ سِكِّينًا وَقَالَتِ ٱخْرُجْ عَلَيْهِنَّ ۖ فَلَمَّا رَأَيْنَهُۥٓ أَكْبَرْنَهُۥ وَقَطَّعْنَ
أَيْدِيَهُنَّ وَقُلْنَ حَٰشَ لِلَّهِ مَا هَٰذَا بَشَرًا إِنْ هَٰذَآ إِلَّا مَلَكٌ كَرِيمٌ ﴿٣١﴾ قَالَتْ فَذَٰلِكُنَّ ٱلَّذِى
لُمْتُنَّنِى فِيهِ ۖ وَلَقَدْ رَٰوَدتُّهُۥ عَن نَّفْسِهِۦ فَٱسْتَعْصَمَ ۖ وَلَئِن لَّمْ يَفْعَلْ مَآ ءَامُرُهُۥ لَيُسْجَنَنَّ
وَلَيَكُونًا مِّنَ ٱلصَّٰغِرِينَ ﴿٣٢﴾ قَالَ رَبِّ ٱلسِّجْنُ أَحَبُّ إِلَىَّ مِمَّا يَدْعُونَنِىٓ إِلَيْهِ ۖ وَإِلَّا تَصْرِفْ
عَنِّى كَيْدَهُنَّ أَصْبُ إِلَيْهِنَّ وَأَكُن مِّنَ ٱلْجَٰهِلِينَ ﴿٣٣﴾ فَٱسْتَجَابَ لَهُۥ رَبُّهُۥ فَصَرَفَ عَنْهُ
كَيْدَهُنَّ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٣٤﴾

**30-34.** በከተማው ያሉ ሴቶችም የዐዚዝ ሚስት ብላቴናዋን ከነፍሱ ታባብለዋለች። በእውነቱ ፍቅሩ ልቧን መቷታል። እኛ በግልጽ ስሕተት ውስጥ ሆና በእርግጥ እናያታለን አሉ። እሷም ሐሜታቸውን በሰማች ጊዜ የግብዣ ጥሪ ወደነሱ ላከችባቸው። ምግብንም ለእነርሱ አዘጋጀችላቸው። ለያንዳንዳቸውም ቢላዋን ሰጠች። በእነርሱም ላይ ውጣ አለችው። እነርሱም በተመለከቱት ጊዜ በጣም አደነቁት። እጆቻቸዉንም በቢላዋው ከታተፉት። ለአላህ ጥራት ይገባው። ይህ ሰው አይደለም። ይህ ያማረ መልአክ እንጂ ሌላ አይደለም አሉ። በዚህ ጊዜ ይህ እኮ ነው ያ በእርሱ ፍቅር ያማችሁኝ ሰው። በእርግጥም ከነፍሱ አባባልኩት ግና እርሱ እንቢ አለ። ወደፊትም የማዘውንም ነገር ባይሠራ በእርግጥ ይታሰራል ከወራዶቹም ይኾናል አለች። ጌታዬ ሆይ፣ ወደ እርሱ ከሚጠሩኝ ነገር (ከዝሙት) ይልቅ መታሰር ለእኔ የተወደደ ነው። ተንኮላቸውንም ከእኔ ላይ ባትመልስልኝ ወደ እነርሱ እዘነበላለሁ። ከስሕተተኞቹም እሆናለሁ አለ። ጌታው ፀሎቱን ተቀበለው ተንኮላቸውንም ከእርሱ መለሰለት። እነሆ!፣ እርሱ ሰሚና ዐዋቂ ነውና።

ثُمَّ بَدَا لَهُم مِّنۢ بَعْدِ مَا رَأَوُا۟ ٱلْءَايَٰتِ لَيَسْجُنُنَّهُۥ حَتَّىٰ حِينٍ ﴿٣٥﴾ وَدَخَلَ مَعَهُ ٱلسِّجْنَ فَتَيَانِ ۖ
قَالَ أَحَدُهُمَآ إِنِّىٓ أَرَىٰنِىٓ أَعْصِرُ خَمْرًا ۖ وَقَالَ ٱلْءَاخَرُ إِنِّىٓ أَرَىٰنِىٓ أَحْمِلُ فَوْقَ رَأْسِى خُبْزًا تَأْكُلُ

ٱلطَّيْرُ مِنْهُ ۖ نَبِّئْنَا بِتَأْوِيلِهِۦٓ ۖ إِنَّا نَرَىٰكَ مِنَ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٣٦﴾ قَالَ لَا يَأْتِيكُمَا طَعَامٌ تُرْزَقَانِهِۦٓ
إِلَّا نَبَّأْتُكُمَا بِتَأْوِيلِهِۦ قَبْلَ أَن يَأْتِيَكُمَا ۚ ذَٰلِكُمَا مِمَّا عَلَّمَنِى رَبِّىٓ ۚ إِنِّى تَرَكْتُ مِلَّةَ قَوْمٍ
لَّا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَهُم بِٱلْـَٔاخِرَةِ هُمْ كَٰفِرُونَ ﴿٣٧﴾ وَٱتَّبَعْتُ مِلَّةَ ءَابَآءِىٓ إِبْرَٰهِيمَ وَإِسْحَٰقَ
وَيَعْقُوبَ ۚ مَا كَانَ لَنَآ أَن نُّشْرِكَ بِٱللَّهِ مِن شَىْءٍ ۚ ذَٰلِكَ مِن فَضْلِ ٱللَّهِ عَلَيْنَا وَعَلَى ٱلنَّاسِ
وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَشْكُرُونَ ﴿٣٨﴾ يَٰصَٰحِبَىِ ٱلسِّجْنِ ءَأَرْبَابٌ مُّتَفَرِّقُونَ خَيْرٌ أَمِ
ٱللَّهُ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّارُ ﴿٣٩﴾ مَا تَعْبُدُونَ مِن دُونِهِۦٓ إِلَّآ أَسْمَآءً سَمَّيْتُمُوهَآ أَنتُمْ وَءَابَآؤُكُم مَّآ
أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا مِن سُلْطَٰنٍ ۚ إِنِ ٱلْحُكْمُ إِلَّا لِلَّهِ ۚ أَمَرَ أَلَّا تَعْبُدُوٓا۟ إِلَّآ إِيَّاهُ ۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ
وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٤٠﴾

**35-40.** ከዚያ ማስረጃዎችን ካዩ በኋላ እስከ ጊዜ ድረስ እንዲያስሩት ለእነርሱ ታያቸው። ከእሱም ጋር ሁለት ጐበዞች እስር ቤቱ ገቡ። አንደኛቸው እኔ በሕልሜ የወይን ጠጅን ስጠምቅ አየሁ አለ። ሌላው ደግሞ እኔ በራሴ ላይ ዳቦ ተሸክሜ ከእሱ በራሪ አሞራ ስትበላ አየሁ ፍችውን ንገረን እኛ ከአሳማሪዎች ሁነህ እናይሃለንና አሉት። ዩሱፍም አለ ማንኛውም የምትሰጡት ምግብ ለእናንተ ከመምጣቱ በፊት ፍችውን የምነግራችሁ ቢሆን እንጂ አይመጣላችሁም። ይህ ጉዳይ ጌታዬ ካሳወቀኝ ነገር ከፊሉ ነው። እኔም በአላህ የማያምኑትንና በመጨረሻይቱ ዓለም ከሓዲያን የሆኑ ሕዝቦችን ሃይማኖት ትቻለሁ። የአባቶቼን የኢብራሂምንና የኢስሐቅን፤ የያዕቁብን ሃይማኖት ተከትያለሁ። ለእኛ በአላህ ምንንም ማጋራት አይገባንም። ያ! አለማጋራት በእኛ ላይና በሰዎች ላይ የአላህ ችሮታ ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያመሰግኑም። የእስር ቤት ጓደኞቼ ሆይ፣ የተለያዩ አምላኮች ይሻላሉን ወይስ አሸናፊውና አንዱ አላህ? ከእርሱ ሌላ እናንተና አባቶቻችሁ አማልክት ብላችሁ የጠራችኋቸውን ስሞች እንጂ አትገዙም አላህ በእርሷ ምንም አስረጂ አላወረደም ፍርዱ የአላህ እንጂ የሌላ አይደለም። እርሱን እንጂ ሌላን እንዳትገዙ አዟል። ይህ ትክክለኛው ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።

يَٰصَٰحِبَىِ ٱلسِّجْنِ أَمَّآ أَحَدُكُمَا فَيَسْقِى رَبَّهُۥ خَمْرًا ۖ وَأَمَّا ٱلْـَٔاخَرُ فَيُصْلَبُ فَتَأْكُلُ ٱلطَّيْرُ
مِن رَّأْسِهِۦ ۚ قُضِىَ ٱلْأَمْرُ ٱلَّذِى فِيهِ تَسْتَفْتِيَانِ ﴿٤١﴾ وَقَالَ لِلَّذِى ظَنَّ أَنَّهُۥ نَاجٍ مِّنْهُمَا ٱذْكُرْنِى
عِندَ رَبِّكَ فَأَنسَىٰهُ ٱلشَّيْطَٰنُ ذِكْرَ رَبِّهِۦ فَلَبِثَ فِى ٱلسِّجْنِ بِضْعَ سِنِينَ ﴿٤٢﴾

**41-42.** የወህኒ ቤት ጓደኞቼ ሆይ! አንደኛችሁማ ንጉሡን ጠጅ ያጠጣል። ሌላውማ ይሰቀላል። ከራሱም በራሪ አሞራ ትበላለች። ያ ፍቹን የምትጠይቁት ነገር ተፈፀመ (አላቸው)። ለዚያም ከሁለቱ እርሱ የሚድን መኾኑን ለተጠራጠረው ጌታህ ዘንድ አስታውሰኝ አለው። ጌታውንም ከማስታወስ ሰይጣን አስረሳው ለጥቂት ዓመታትም በወህኒ ቤቱ ውስጥ ቆየ።

وَقَالَ ٱلۡمَلِكُ إِنِّيٓ أَرَىٰ سَبۡعَ بَقَرَٰتٖ سِمَانٖ يَأۡكُلُهُنَّ سَبۡعٌ عِجَافٞ وَسَبۡعَ سُنۢبُلَٰتٍ خُضۡرٖ
وَأُخَرَ يَابِسَٰتٖۖ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمَلَأُ أَفۡتُونِي فِي رُءۡيَٰيَ إِن كُنتُمۡ لِلرُّءۡيَا تَعۡبُرُونَ ٤٣ قَالُوٓاْ أَضۡغَٰثُ
أَحۡلَٰمٖۖ وَمَا نَحۡنُ بِتَأۡوِيلِ ٱلۡأَحۡلَٰمِ بِعَٰلِمِينَ ٤٤ وَقَالَ ٱلَّذِي نَجَا مِنۡهُمَا وَٱدَّكَرَ بَعۡدَ أُمَّةٍ أَنَا۠
أُنَبِّئُكُم بِتَأۡوِيلِهِۦ فَأَرۡسِلُونِ ٤٥ يُوسُفُ أَيُّهَا ٱلصِّدِّيقُ أَفۡتِنَا فِي سَبۡعِ بَقَرَٰتٖ سِمَانٖ
يَأۡكُلُهُنَّ سَبۡعٌ عِجَافٞ وَسَبۡعِ سُنۢبُلَٰتٍ خُضۡرٖ وَأُخَرَ يَابِسَٰتٖ لَّعَلِّيٓ أَرۡجِعُ إِلَى ٱلنَّاسِ
لَعَلَّهُمۡ يَعۡلَمُونَ ٤٦ قَالَ تَزۡرَعُونَ سَبۡعَ سِنِينَ دَأَبٗا فَمَا حَصَدتُّمۡ فَذَرُوهُ فِي سُنۢبُلِهِۦٓ إِلَّا
قَلِيلٗا مِّمَّا تَأۡكُلُونَ ٤٧ ثُمَّ يَأۡتِي مِنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ سَبۡعٞ شِدَادٞ يَأۡكُلۡنَ مَا قَدَّمۡتُمۡ لَهُنَّ إِلَّا
قَلِيلٗا مِّمَّا تُحۡصِنُونَ ٤٨ ثُمَّ يَأۡتِي مِنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ عَامٞ فِيهِ يُغَاثُ ٱلنَّاسُ وَفِيهِ يَعۡصِرُونَ ٤٩

**43-49.** ንጉሡም እኔ ሰባት የሰቡ ላሞችን ሰባት የከሱ ላሞች ሲበሉዋቸው፣ ሰባት ለምለም ዘለላዎችንም ሌሎች ሰባት ደረቆችን ስብርብር ሲያደርጉ በሕልሜ አየሁ። እናንተ ታላላቅ ሰዎች ሆይ፣ ሕልም መፍታት የምታውቁ ከሆናችሁ ሕልሜን ፍቱልኝ አላቸው። ሕልሞችህ ቅዠቶች ናቸው። እኛም የሕልሞችን ፍች ዐዋቂዎች አይደለንም አሉት። ያም ከሁለቱ መካከል የዳነውና ከብዙ ጊዜ በኋላ ዩሱፍን ያስታወሰው ሰው እኔ ፍቹን እነግራችኋለሁና ላኩኝ አለ። አንተ እውነተኛው ዩሱፍ ሆይ፣ ሰባትን የሰቡ ላሞች ሰባት ከሲታዎች ላሞች ሲበሏቸው፤ ሰባትን ለምለም ዘለላዎችም ሌሎችን ሰባት ደረቆች በእነርሱ ላይ ሲያሸነፉ ያየን ሰው ሕልም ፍች እስቲ ተችልን። ያውቁ ዘንድ ወደ ሰዎቹ ልመለስ እከጅላለሁና አለው። እርሱም አለ ሰባትን የተከታተሉ ዓመታት ትዘራላችሁ ያጨዳችሁትንም ሁሉ ከምትበሉት ጥቂት በስተቀር በዘለላው ውስጥ ተውት። ከዚያ ከነዚያ በኋላ ካደለባችሁት ጥቂት ሲቀር ለእነርሱ ያደለባችሁትን ሁሉ የሚበሉ ሰባት የችግር ዓመታት ይመጣሉ። ከዚያ ከእነዚያ በኋላ ሰዎቹ በእርሱ ዝናብ እንደልባቸው የሚያገኙበትና በእርሱም ወይንን የሚጨምቁበት ዓመት ይመጣል።

وَقَالَ ٱلۡمَلِكُ ٱئۡتُونِي بِهِۦۖ فَلَمَّا جَآءَهُ ٱلرَّسُولُ قَالَ ٱرۡجِعۡ إِلَىٰ رَبِّكَ فَسۡـَٔلۡهُ مَا بَالُ ٱلنِّسۡوَةِ
ٱلَّٰتِي قَطَّعۡنَ أَيۡدِيَهُنَّۚ إِنَّ رَبِّي بِكَيۡدِهِنَّ عَلِيمٞ ﴿٥٠﴾ قَالَ مَا خَطۡبُكُنَّ إِذۡ رَٰوَدتُّنَّ يُوسُفَ
عَن نَّفۡسِهِۦۚ قُلۡنَ حَٰشَ لِلَّهِ مَا عَلِمۡنَا عَلَيۡهِ مِن سُوٓءٖۚ قَالَتِ ٱمۡرَأَتُ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡـَٰٔنَ
حَصۡحَصَ ٱلۡحَقُّ أَنَا۠ رَٰوَدتُّهُۥ عَن نَّفۡسِهِۦ وَإِنَّهُۥ لَمِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴿٥١﴾ ذَٰلِكَ لِيَعۡلَمَ أَنِّي لَمۡ
أَخُنۡهُ بِٱلۡغَيۡبِ وَأَنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي كَيۡدَ ٱلۡخَآئِنِينَ ﴿٥٢﴾ ۞وَمَآ أُبَرِّئُ نَفۡسِيٓۚ إِنَّ ٱلنَّفۡسَ
لَأَمَّارَةُۢ بِٱلسُّوٓءِ إِلَّا مَا رَحِمَ رَبِّيٓۚ إِنَّ رَبِّي غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٥٣﴾

**50-53.** ንጉሡም እርሱን አምጡልኝ አለ። መልእክተኛውም ወደ ዩሱፍ በመጣ ጊዜ ዩሱፍ ወደ ጌታህ ተመለስና የእነዚያን እጆቻቸውን የቆረጡትን ሴቶች ሁኔታ ጠይቀው ጌታዬ ተንኮላቸውን ዐዋቂ ነውና አለው። ንጉሡም ዩሱፍን ከነፍሱ ባባበላችሁት ጊዜ ነገራችሁ ምንድን ነው? አላቸው ለአላህ ጥራት ይገባው በእርሱ ላይ ምንም መጥፎን ነገር አላወቅንም (አላየንም) አሉት። የዐዚዝ ሚስት አሁን እውነቱ ተገለፀ እኔ ከነፍሱ አባበልኩት እርሱም ከእውነተኞቹ ነው አለች። ዩሱፍ ይህ ጌታዬ ሩቅ ሆኖ ሳለ ያልከዳሁት መሆኔንና አላህም የከዳተኞችን* ተንኮል የማያቃና መሆኑን እንዲያውቅ ነው አለ። ነፍሴንም (ከስሕተት) አላጠራም። ነፍስ ሁሉ ጌታዬ የጠበቃት ካልኾነች በስተቀር በመጥፎ ነገር በእርግጥ አዛዥ ናትና። ጌታዬ በጣም መሐሪና አዛኝ ነው አለ።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም ከዳተኛ በትንሳኤ ቀን ይዞት የሚነሳው ልዩ ባንዲራ አለው። እንዲህም ይባላል «ይህ ከዳተኛ የከዳተኛ ልጅ ነው»

وَقَالَ ٱلۡمَلِكُ ٱئۡتُونِي بِهِۦٓ أَسۡتَخۡلِصۡهُ لِنَفۡسِيۖ فَلَمَّا كَلَّمَهُۥ قَالَ إِنَّكَ ٱلۡيَوۡمَ لَدَيۡنَا مَكِينٌ
أَمِينٞ ﴿٥٤﴾ قَالَ ٱجۡعَلۡنِي عَلَىٰ خَزَآئِنِ ٱلۡأَرۡضِۖ إِنِّي حَفِيظٌ عَلِيمٞ ﴿٥٥﴾

**54-55.** ንጉሡም እርሱን አምጡልኝ ለራሴ ግለኛ (ብቻ) አደርገዋለሁና አለ ባናገረውም ጊዜ አንተ ዛሬ እኛ ዘንድ ባለሟል። ታማኝ ነህ አለው። በምድር ግምጃ ቤቶች ላይ ሹም አድርገኝ እኔ ጠባቂ ዐዋቂ ነኝና አለ።

وَكَذَٰلِكَ مَكَّنَّا لِيُوسُفَ فِي ٱلۡأَرۡضِ يَتَبَوَّأُ مِنۡهَا حَيۡثُ يَشَآءُۚ نُصِيبُ بِرَحۡمَتِنَا مَن نَّشَآءُۖ
وَلَا نُضِيعُ أَجۡرَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٥٦﴾ وَلَأَجۡرُ ٱلۡأٓخِرَةِ خَيۡرٞ لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَكَانُواْ يَتَّقُونَ ﴿٥٧﴾ وَجَآءَ
إِخۡوَةُ يُوسُفَ فَدَخَلُواْ عَلَيۡهِ فَعَرَفَهُمۡ وَهُمۡ لَهُۥ مُنكِرُونَ ﴿٥٨﴾ وَلَمَّا جَهَّزَهُم بِجَهَازِهِمۡ قَالَ

ٱئۡتُونِي بِأَخٖ لَّكُم مِّنۡ أَبِيكُمۡۚ أَلَا تَرَوۡنَ أَنِّيٓ أُوفِي ٱلۡكَيۡلَ وَأَنَا۠ خَيۡرُ ٱلۡمُنزِلِينَ ٥٩ فَإِن لَّمۡ
تَأۡتُونِي بِهِۦ فَلَا كَيۡلَ لَكُمۡ عِندِي وَلَا تَقۡرَبُونِ ٦٠ قَالُواْ سَنُرَٰوِدُ عَنۡهُ أَبَاهُ وَإِنَّا لَفَٰعِلُونَ ٦١

**56-61.** እንደዚሁም ለዩሱፍ በምድር ላይ ከእርሷ በፈለገው ስፍራ የሚሰፍር ሲኾን አስመቸነው በችግሮቻችን የምንሻውን ሰው እንለያለን የበጎ ሠሪዎችንም ዋጋ አናጠፋም። የመጨረሻይቱም ዓለም ምንዳ ለነዚያ ላመኑትና ይጠነቀቁ ለነበሩት የበለጠ ነው። የዩሱፍ ወንድሞችም መጡ በርሱም ላይ ገቡ እነርሱም እርሱን የሳቱት ሲሆኑ አወቃቸው። ጉዳያቸውን ፈጽሞ ስንቃቸውንም ባዘጋጀላቸው ጊዜ አለ። ከአባታችሁ በኩል የሆነውን ወንድማችሁን አምጡልኝ እኔ ከአስተናጋጆች ሁሉ በላጭ ስሆን ስፍርን የምሞላ መሆኔን አታዩምን? እርሱን ባታመጡልኝ እኔ ዘንድ ለናነተ ስፍር የላችሁም አትቀርቡኝምም። ስለ እርሱ አባቱን በጥብቅ እንጠይቃለን እኛም ይህንን በእርግጥ ሰሪዎች ነን አሉት።

وَقَالَ لِفِتۡيَٰنِهِ ٱجۡعَلُواْ بِضَٰعَتَهُمۡ فِي رِحَالِهِمۡ لَعَلَّهُمۡ يَعۡرِفُونَهَآ إِذَا ٱنقَلَبُوٓاْ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِمۡ لَعَلَّهُمۡ
يَرۡجِعُونَ ٦٢ فَلَمَّا رَجَعُوٓاْ إِلَىٰٓ أَبِيهِمۡ قَالُواْ يَٰٓأَبَانَا مُنِعَ مِنَّا ٱلۡكَيۡلُ فَأَرۡسِلۡ مَعَنَآ أَخَانَا
نَكۡتَلۡ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٦٣ قَالَ هَلۡ ءَامَنُكُمۡ عَلَيۡهِ إِلَّا كَمَآ أَمِنتُكُمۡ عَلَىٰٓ أَخِيهِ مِن
قَبۡلُ فَٱللَّهُ خَيۡرٌ حَٰفِظٗاۖ وَهُوَ أَرۡحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ٦٤ وَلَمَّا فَتَحُواْ مَتَٰعَهُمۡ وَجَدُواْ بِضَٰعَتَهُمۡ
رُدَّتۡ إِلَيۡهِمۡۖ قَالُواْ يَٰٓأَبَانَا مَا نَبۡغِيۖ هَٰذِهِۦ بِضَٰعَتُنَا رُدَّتۡ إِلَيۡنَاۖ وَنَمِيرُ أَهۡلَنَا وَنَحۡفَظُ أَخَانَا
وَنَزۡدَادُ كَيۡلَ بَعِيرٖۖ ذَٰلِكَ كَيۡلٞ يَسِيرٞ ٦٥

**62-65.** ለአሽከሮቹ፡- ሸቀጣቸውን ወደ ቤተሰቦቻቸው በተመለሱ ጊዜ ያውቋት ዘንድ በየዓዞቻቸው ውስጥ አድርጉላቸው ሊመለሱ ይከጀላልና አላቸው። ወደ አባታቸውም በተመለሱ ጊዜ፡- አባታችን ሆይ፤ ወንድማችንን እስከምንወስድ ስፍር ከኛ ተከልክሏል። ስለዚህ ወንድማችንን ከእኛ ጋር ላከው ይሰፈርልናልና እኛም ለእርሱ ጠባቂዎች ነን አሉ። ከአሁን በፊት በወንድሙ ላይ እንዳመንኳችሁ እንጅ በእርሱ ላይ አምናችኋለሁን? አላህም በጠባቂነት ከሁሉ የበለጠ ነው። እርሱም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነው አላቸው። እቃቸውንም በከፈቱ ጊዜ ሸቀጣቸውን ወደ እነርሱ ተመልሶ አገኙት። አባታችን ሆይ፣ ምን እንፈልጋለን? ይህች ሸቀጣችን ናት ወደ እኛ ተመልሳልናለች (እንረዳባታለን)። ለቤተሰቦቻችንም እንሸምታለን ወንድማችንንም እንጠብቃለን። የግመልን ጭነት እንጨምራለን። ይህ በንጉሱ ላይ ቀላል ስፍር ነው አሉ።

قَالَ لَنْ أُرْسِلَهُۥ مَعَكُمْ حَتَّىٰ تُؤْتُونِ مَوْثِقًا مِّنَ ٱللَّهِ لَتَأْتُنَّنِى بِهِۦٓ إِلَّآ أَن يُحَاطَ بِكُمْ ۖ فَلَمَّآ
ءَاتَوْهُ مَوْثِقَهُمْ قَالَ ٱللَّهُ عَلَىٰ مَا نَقُولُ وَكِيلٌ ﴿٦٦﴾ وَقَالَ يَٰبَنِىَّ لَا تَدْخُلُوا۟ مِنۢ بَابٍ وَٰحِدٍ
وَٱدْخُلُوا۟ مِنْ أَبْوَٰبٍ مُّتَفَرِّقَةٍ ۖ وَمَآ أُغْنِى عَنكُم مِّنَ ٱللَّهِ مِن شَىْءٍ ۖ إِنِ ٱلْحُكْمُ إِلَّا لِلَّهِ ۖ
عَلَيْهِ تَوَكَّلْتُ ۖ وَعَلَيْهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُتَوَكِّلُونَ ﴿٦٧﴾ وَلَمَّا دَخَلُوا۟ مِنْ حَيْثُ أَمَرَهُمْ أَبُوهُم مَّا كَانَ
يُغْنِى عَنْهُم مِّنَ ٱللَّهِ مِن شَىْءٍ إِلَّا حَاجَةً فِى نَفْسِ يَعْقُوبَ قَضَىٰهَا ۚ وَإِنَّهُۥ لَذُو عِلْمٍ لِّمَا
عَلَّمْنَٰهُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٦٨﴾

**66-68.** ካልተከበባችሁ በስተቀር እርሱን በእርግጥ የምታመጡልኝ ለመሆናችሁ ከአላህ የሆነን ቃልኪዳን (መተማመኛ) እስከምትሰጡኝ ድረስ ከናንተ ጋር ፈጽሞ አልከውም አላቸው። መተማመኛቸውንም በሰጡ ጊዜ አላህ በምንለው ሁሉ ላይ ምስክር ነው አላቸው። አለም:- ልጆቼ ሆይ!፤ በአንድ በር አትግቡ። ግን በተለያዩ በሮች ግቡ። ከአላህም ፍርድ በምንም አልጠቅማችሁም (አልመልስላችሁም) ፍርዱ የአላህ እንጂ የሌላ አይደለም።* በእርሱ ላይ ብቻ ተመካሁ ተመኪዎችም ሁሉ በእርሱ ላይ ብቻ ይመኩ። አባታቸው ካዘዛቸው ስፍራ በገቡ ጊዜ ከአላህ ፍርድ ምንም ነገር ከእነርሱ የሚከለክልላቸው አልነበረም። ግን በየዕቁብ ነፍስ ውስጥ የነበረች ጉዳይ ናት። ፈፀማት እርሱም ስላሳወቅነው የእውቀት ባለቤት ነው ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-

(ሀ) «ሰባ ሺህ የሚሆነው የኔ ሕዝቦች ካለምንም ጥያቄ ጀነት ይገባሉ። እነዚህ ሰዎች ሩቅያህን የማይሰሩ፤ በነገሮች መጥፎ የገፅ ምልክቶችን የማያዩ፤ መመካታቸውን በአላህ ላይ ብቻ የሚያደርጉ ናቸው» «ሩቅያህ» ማለት ከቁርኣን የተወሰኑ ምዕራፎችንና አናቅፅ ካነበቡ በኋላ በበሽተኛው ሰውነት ላይ ምራቅ በመትፋት የመፈወስ ዘዴ ነው።

(ለ) አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «አንድ አይሁዳዊ ለአንድ አይሁዳዊ አንድ ሺህ ዲናር እንዲያበድረው ጠየቀው። አበዳሪውም «የማስመሰክራቸውን ሰዎች አምጣልኝ» አለው። ተበዳሪውም «ለምስክርነት አላህ ከማንም በላይ በቂ ነው አለው» አበዳሪውም «እውነትህን ነው» በማለት። በተወሰነ ጊዜ የሚመለስ ዲናር አበደረው። የብድር መክፈያውንም ቀን ወሰኑ። ሆኖም አበዳሪው በተቀጣጠሩበት ቀን ለስራ ጉዳይ ርቆ ሄዶ ስለነበር ተበዳሪው ብድሩን በጊዜው ለመክፈል ይችል ዘንድ ወደ አበዳሪው የሚሄድበትን መርከብ ሲያፈላልግ ምንም አይነት መርከብ አላገኘም። አንድ ቁራጭ እንጨት አምጥቶ ውስጡን ከቦረቦረ በኋላ አንድ ሺህ ዲናርና ትንሽ መልዕክት በቦረቦረው እንጨት ውስጥ ከትቶ ቀዳዳውን ዘጋው። ወደ ባህርም ሄዶ «ጌታዬ ሆይ! እኔ ከእከሌ አንድ ሺህ ዲናር መበደሬን የሚመሰክር ሰው አምጣ ስባል ለምስክርነት ከሁሉም በላይ አላህ በቂ ነው ማለቴንና የአንተን ምስክርነትም መውደዱን ታውቃለህ። መርከብ አግኝቼ ገንዘቡን ልልክለት ሞክሬ አልቻልኩም። ይህን ገንዘብ ላንተ ትቼልሃለሁ» ብሎ እንጨቱን

*ወደ ባህሩ ወረወረው። ከዚያም ከባህሩ ርቆ ወደ አበዳሪው መንደር የሚሄድበትን መርከብ መፈለግ ጀመረ። ያ ገንዘብ ያበደረው ሰው ወደ ባህሩ ሂዶ ከአሁን አሁን አንዲት መርከብ ገንዘቤን ታመጣለች ብሎ ሲጠባበቅ አንዲት እንጨት ተመለከተና ለቤተሰቦቹ ለማገዶ ትሆናለች በማለት እንጨቷን ይዟት ሄደ። ቤቱ ደርሶ እንጨቱን ሲፈልጠው ገንዘቡንና የተፃፈውን ወረቀት አገኘ። የተበደረውም ሰውም ወደርሱ አንድ ሺህ ዲናሩን ይዞ መጣና «በአላህ እምላለሁ! ገንዘብህን በቀጠሮው ቀን ይዤልህ ለመምጣት መርከቦችን ማፈላለጌን አላቆምኩም ነበር። አሁን ከመጣሁበት መርከብ በፊት አንድም መርከብ አላገኘሁም» አለው። አበዳሪው «ወደኔ አንድ ነገር ልከህ ነበርን?» ሲል ጠየቀው። ተበዳሪውም «አሁን ከመጣሁበት በፊት አንድም መርከብ አላገኘሁም እያልኩህ!» ሲል በመገረም መለሰለት። አበዳሪው «አላህ በእርግጥ በእንጨት ውስጥ የላከውን ሰጥቶልሃልና አንድ ሺህ ዲናርህን ይዘህ ሂድ» አለው»።*

وَلَمَّا دَخَلُواْ عَلَىٰ يُوسُفَ ءَاوَىٰٓ إِلَيۡهِ أَخَاهُۖ قَالَ إِنِّيٓ أَنَا۠ أَخُوكَ فَلَا تَبۡتَئِسۡ بِمَا كَانُواْ
يَعۡمَلُونَ ٦٩ فَلَمَّا جَهَّزَهُم بِجَهَازِهِمۡ جَعَلَ ٱلسِّقَايَةَ فِي رَحۡلِ أَخِيهِ ثُمَّ أَذَّنَ مُؤَذِّنٌ أَيَّتُهَا
ٱلۡعِيرُ إِنَّكُمۡ لَسَٰرِقُونَ ٧٠ قَالُواْ وَأَقۡبَلُواْ عَلَيۡهِم مَّاذَا تَفۡقِدُونَ ٧١ قَالُواْ نَفۡقِدُ صُوَاعَ
ٱلۡمَلِكِ وَلِمَن جَآءَ بِهِۦ حِمۡلُ بَعِيرٖ وَأَنَا۠ بِهِۦ زَعِيمٞ ٧٢ قَالُواْ تَٱللَّهِ لَقَدۡ عَلِمۡتُم مَّا جِئۡنَا
لِنُفۡسِدَ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا كُنَّا سَٰرِقِينَ ٧٣ قَالُواْ فَمَا جَزَٰٓؤُهُۥٓ إِن كُنتُمۡ كَٰذِبِينَ ٧٤ قَالُواْ
جَزَٰٓؤُهُۥ مَن وُجِدَ فِي رَحۡلِهِۦ فَهُوَ جَزَٰٓؤُهُۥۚ كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلظَّٰلِمِينَ ٧٥

**69-75.** በዩሱፍ ላይ በገቡ ጊዜም ወንድሙን ወደ እርሱ አስጠጋውና እነሆ እኔ ወንድምህ ነኝ ይሰሩት በነበሩትም ሁሉ አትቆላጭ (አትበሳጭ) አለው። እቃቸውን ባዘጋጀላቸው ጊዜ ዋንጫይቱን በወንድሙ እቃ ውስጥ አደረገ ከዚያ እናንተ ባለ ግመሎች ሆይ፣ እናንተ በእርግጥ ሌቦች ናችሁ። ሲል ጠሪ ተጣራ። ወደ እነርሱ ዞረውም። ምንድን ጠፋችሁ? አሉ። የንጉሱ መስፈሪያ ጠፍቶናል እርሱንም ላመጣ ሰው የግመል ጭነት አለው እኔም በእርሱ ተያዥ ነኝ አለ። በአላህ እንምላለን በምድር ላይ ለማጥፋት እንዳልመጣን በእርግጥ አውቃችኋል ሌቦችም አልነበርንም አሉ። ውሸታሞች ብትሆኑ ቅጣቱ ምንድን ነው? አሏቸው። ቅጣቱ በየዕቁብ ሕግ እቃው በጓዙ ውስጥ የተገኘበት ሰው ራሱ ባሪያ ተደርጎ መውሰድ ነው። እርሱም ቅጣቱ ነው። ልክ እንደዚሁ በደለኞችን እንቀጣለን አሉ።

فَبَدَأَ بِأَوۡعِيَتِهِمۡ قَبۡلَ وِعَآءِ أَخِيهِ ثُمَّ ٱسۡتَخۡرَجَهَا مِن وِعَآءِ أَخِيهِۚ
كَذَٰلِكَ كِدۡنَا لِيُوسُفَۖ مَا كَانَ لِيَأۡخُذَ أَخَاهُ فِي دِينِ ٱلۡمَلِكِ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُۚ
نَرۡفَعُ دَرَجَٰتٖ مَّن نَّشَآءُۗ وَفَوۡقَ كُلِّ ذِي عِلۡمٍ عَلِيمٞ ٧٦

76. (ምርመራውን) ከወንድሙ እቃ በፊት በእቃዎቻቸው ጀመረ። ከዚያ ዋንጫይቱን ከወንድሙ እቃ ውስጥ አወጣት እንደዚሁ ለዩሱፍ ብልሃትን አስተማርነው። አላህ ባልሻ ኖሮ በንጉሱ ሕግ ወንድሙን ሊይዝ አይገባውም ነበር። የምንሻውን ሰው በደረጃዎች ከፍ እናደርጋለን ከእውቀት ባለቤቶች ሁሉ በላይም ዐዋቂ አለ።

۞قَالُوٓاْ إِن يَسۡرِقۡ فَقَدۡ سَرَقَ أَخٞ لَّهُۥ مِن قَبۡلُۚ فَأَسَرَّهَا يُوسُفُ فِي نَفۡسِهِۦ وَلَمۡ يُبۡدِهَا لَهُمۡۚ قَالَ أَنتُمۡ شَرّٞ مَّكَانٗاۖ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا تَصِفُونَ ﴿٧٧﴾ قَالُواْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡعَزِيزُ إِنَّ لَهُۥٓ أَبٗا شَيۡخٗا كَبِيرٗا فَخُذۡ أَحَدَنَا مَكَانَهُۥٓۖ إِنَّا نَرَىٰكَ مِنَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٧٨﴾ قَالَ مَعَاذَ ٱللَّهِ أَن نَّأۡخُذَ إِلَّا مَن وَجَدۡنَا مَتَٰعَنَا عِندَهُۥٓ إِنَّآ إِذٗا لَّظَٰلِمُونَ ﴿٧٩﴾

77-79. እርሱ ቢሰርቅ ከአሁን በፊት የእርሱው ወንድም በእርግጥ ሰርቋል አሉ። ዩሱፍም ይህችን አስቀያሚ ንግግር በነፍሱ ውስጥ ደበቃት። ለእነርሱም አልገለጣትም (በልቡ) እናንተ ሥራችሁ የከፋ ነው። አላህ የምትሉትን ሁሉ ይበልጥ አዋቂ ነው አለ። አንተ የተከበርከው ሆይ፣ ለእርሱ በእርግጥ ታላቅ ሽማግሌ አባት አለው። ስለዚህ በእርሱ ስፍራ አንደኛችንን ያዝ። እኛ ከመልካም ሠሪዎች ሆነህ እናይሃለንና አሉት። ዕቃችንን እርሱ ዘንድ ያገኘንበትን ሰው እንጂ ሌላን ከመያዝ በአላህ እንጠበቃለን። እኛ ያን ባደረግን ጊዜ በእርግጥ በዳዮች ነን አለ።

فَلَمَّا ٱسۡتَيۡـَٔسُواْ مِنۡهُ خَلَصُواْ نَجِيّٗاۖ قَالَ كَبِيرُهُمۡ أَلَمۡ تَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ أَبَاكُمۡ قَدۡ أَخَذَ عَلَيۡكُم مَّوۡثِقٗا مِّنَ ٱللَّهِ وَمِن قَبۡلُ مَا فَرَّطتُمۡ فِي يُوسُفَۖ فَلَنۡ أَبۡرَحَ ٱلۡأَرۡضَ حَتَّىٰ يَأۡذَنَ لِيٓ أَبِيٓ أَوۡ يَحۡكُمَ ٱللَّهُ لِيۖ وَهُوَ خَيۡرُ ٱلۡحَٰكِمِينَ ﴿٨٠﴾ ٱرۡجِعُوٓاْ إِلَىٰٓ أَبِيكُمۡ فَقُولُواْ يَٰٓأَبَانَآ إِنَّ ٱبۡنَكَ سَرَقَ وَمَا شَهِدۡنَآ إِلَّا بِمَا عَلِمۡنَا وَمَا كُنَّا لِلۡغَيۡبِ حَٰفِظِينَ ﴿٨١﴾ وَسۡـَٔلِ ٱلۡقَرۡيَةَ ٱلَّتِي كُنَّا فِيهَا وَٱلۡعِيرَ ٱلَّتِيٓ أَقۡبَلۡنَا فِيهَاۖ وَإِنَّا لَصَٰدِقُونَ ﴿٨٢﴾ قَالَ بَلۡ سَوَّلَتۡ لَكُمۡ أَنفُسُكُمۡ أَمۡرٗاۖ فَصَبۡرٞ جَمِيلٌۖ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَأۡتِيَنِي بِهِمۡ جَمِيعًاۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡحَكِيمُ ﴿٨٣﴾

80-83. ከእርሱም ተስፋን በቆረጡ ጊዜ የሚመካከሩ ሆነው ገለል አሉ። ታላቃቸው አለ። አባታችሁ በእናንተ ላይ ከአላህ የሆነን መተማመኛ ቃል ኪዳን በእርግጥ የያዘባችሁ መሆኑንና ከዚህም በፊት በዩሱፍ ላይ ግፍ

የሠራችሁትን አታውቁምን? ስለዚህ አባቴ ለእኔ እስከሚፈቅድልኝ ወይም አላህ ለእኔ እስከሚፈርድልኝ ድረስ የምስርን (የግብጽን) ምድር አልለይም። እርሱ ከፈራጆች ሁሉ በላጭ ነው። ወደ አባታችሁ ተመለሱ። በሉትም አባታችን ሆይ ልጅህ ሰረቀ፤ ባወቅነውም ነገር እንጂ አልመሰከርንም ሩቁንም ነገር ምስጢሩን ዐዋቂዎች አልነበርንም። ያችንም በውስጧ የነበርንባትን ከተማ ያችንም በውስጧ የመጣነውን ባለ ግመል ጓድ ጠይቅ እኛም በእርግጥ እውነተኞች ነን። የዕቆብ፡- አይደለም ነፍሶቻችሁ አንዳች ነገርን ለእናንተ ሸለሙላቸሁና ሠራችሁት። መልካም ትዕግስት ማድረግ አለብኝ። እነርሱን የተሰበሰቡ ሆነው አላህ ሊያመጣልኝ ይከጀላል። እነሆ እርሱ ዐዋቂ ጥበበኛ ነውና አላቸው።

وَتَوَلَّىٰ عَنۡهُمۡ وَقَالَ يَٰٓأَسَفَىٰ عَلَىٰ يُوسُفَ وَٱبۡيَضَّتۡ عَيۡنَاهُ مِنَ ٱلۡحُزۡنِ فَهُوَ كَظِيمٞ ﴿٨٤﴾
قَالُواْ تَٱللَّهِ تَفۡتَؤُاْ تَذۡكُرُ يُوسُفَ حَتَّىٰ تَكُونَ حَرَضًا أَوۡ تَكُونَ مِنَ ٱلۡهَٰلِكِينَ ﴿٨٥﴾
قَالَ إِنَّمَآ أَشۡكُواْ بَثِّي وَحُزۡنِيٓ إِلَى ٱللَّهِ وَأَعۡلَمُ مِنَ ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٨٦﴾
يَٰبَنِيَّ ٱذۡهَبُواْ فَتَحَسَّسُواْ مِن يُوسُفَ وَأَخِيهِ وَلَا تَاْيۡـَٔسُواْ مِن رَّوۡحِ ٱللَّهِۖ
إِنَّهُۥ لَا يَاْيۡـَٔسُ مِن رَّوۡحِ ٱللَّهِ إِلَّا ٱلۡقَوۡمُ ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴿٨٧﴾

**84-87.** ከነሱም ዞር አለና፡- በዩሱፍ ላይ ዋ ሐዘኔ አለ። ዓይኖቹም ከሐዘን ልቅሶ የተነሳ ነጡ። እርሱም በትካዜ የተሞላ ነው። እነርሱም፡- በአላህ እንምላለን ለጥፋት የቀረብክ እስከምትሆን ወይም ከጠፊዎቹ እስከምትሆን ድረስ ዩሱፍን ከማውሳት አትወገድም አሉ። ጭንቀቴንና ሐዘኔን የማሰሙተው ወደ አላህ ብቻ ነው። ከአላህ በኩል የማታውቁትን ነገር እኔ አውቃለሁና አላቸው። ልጆቼ ሆይ ሂዱ ከዩሱፍና ከወንድሙም ወሬ ተመራመሩ። ከአላህም እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። እነሆ ከአላህ እዝነት ከሓዲያን ህዝቦች እንጂ ማንም ተስፋ አይቆርጥም አለ።

فَلَمَّا دَخَلُواْ عَلَيۡهِ قَالُواْ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡعَزِيزُ مَسَّنَا وَأَهۡلَنَا ٱلضُّرُّ وَجِئۡنَا بِبِضَٰعَةٖ مُّزۡجَىٰةٖ فَأَوۡفِ
لَنَا ٱلۡكَيۡلَ وَتَصَدَّقۡ عَلَيۡنَآۖ إِنَّ ٱللَّهَ يَجۡزِي ٱلۡمُتَصَدِّقِينَ ﴿٨٨﴾ قَالَ هَلۡ عَلِمۡتُم مَّا فَعَلۡتُم
بِيُوسُفَ وَأَخِيهِ إِذۡ أَنتُمۡ جَٰهِلُونَ ﴿٨٩﴾ قَالُوٓاْ أَءِنَّكَ لَأَنتَ يُوسُفُۖ قَالَ أَنَا۠ يُوسُفُ وَهَٰذَآ أَخِيۖ
قَدۡ مَنَّ ٱللَّهُ عَلَيۡنَآۖ إِنَّهُۥ مَن يَتَّقِ وَيَصۡبِرۡ فَإِنَّ ٱللَّهَ لَا يُضِيعُ أَجۡرَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٩٠﴾

**88-90.** በእርሱም ላይ በገቡ ጊዜ አንተ የተከበርከው ሆይ እኛንም ቤተሰቦቻችንንም ጉዳት ደረሰብን እርካሽ ሸቀጥም ይዘን መጥተናል። ስፍርንም ለእኛ ሙላልን። በእኛም ላይ መጽውት። አላህ መጽዋቾችን ይመነዳልና አሉት። እናንተ የማታውቁ በነበራችሁ ጊዜ በዩሱፍና በወንድሙ ላይ የሠራችሁትን ግፍ አወቃችሁን? አላቸው። አንተ በእርግጥ አንተ ዩሱፍ ነህን? አሉት። አዎ እኔ በትክክል ዩሱፍ ነኝ። ይህም ወንድሜ ነው። አላህ በእኛ ላይ በእርግጥ ለገሰልን። እነሆ የሚጠነቀቅና የሚታገስ ሰው (አላህ ይክሰዋል)። አላህ የበጎ አድራጊዎችን ዋጋ አያጠፋምና አለ።

قَالُواْ تَٱللَّهِ لَقَدۡ ءَاثَرَكَ ٱللَّهُ عَلَيۡنَا وَإِن كُنَّا لَخَٰطِـِٔينَ ﴿٩١﴾ قَالَ لَا تَثۡرِيبَ عَلَيۡكُمُ ٱلۡيَوۡمَۖ
يَغۡفِرُ ٱللَّهُ لَكُمۡۖ وَهُوَ أَرۡحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿٩٢﴾ ٱذۡهَبُواْ بِقَمِيصِي هَٰذَا فَأَلۡقُوهُ عَلَىٰ وَجۡهِ أَبِي يَأۡتِ
بَصِيرٗا وَأۡتُونِي بِأَهۡلِكُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿٩٣﴾ وَلَمَّا فَصَلَتِ ٱلۡعِيرُ قَالَ أَبُوهُمۡ إِنِّي لَأَجِدُ رِيحَ يُوسُفَۖ
لَوۡلَآ أَن تُفَنِّدُونِ ﴿٩٤﴾ قَالُواْ تَٱللَّهِ إِنَّكَ لَفِي ضَلَٰلِكَ ٱلۡقَدِيمِ ﴿٩٥﴾ فَلَمَّآ أَن جَآءَ ٱلۡبَشِيرُ
أَلۡقَىٰهُ عَلَىٰ وَجۡهِهِۦ فَٱرۡتَدَّ بَصِيرٗاۖ قَالَ أَلَمۡ أَقُل لَّكُمۡ إِنِّيٓ أَعۡلَمُ مِنَ ٱللَّهِ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٩٦﴾
قَالُواْ يَٰٓأَبَانَا ٱسۡتَغۡفِرۡ لَنَا ذُنُوبَنَآ إِنَّا كُنَّا خَٰطِـِٔينَ ﴿٩٧﴾ قَالَ سَوۡفَ أَسۡتَغۡفِرُ لَكُمۡ رَبِّيٓۖ إِنَّهُۥ
هُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٩٨﴾

**91-98.** በአላህ እንምላለን አላህ በእኛ ላይ በእርግጥ አበለጠህ፤ እኛም በእርግጥ አጥፊዎች ነበርን አሉ። ዛሬ በእናንተ ላይ ወቀሳ የለባችሁም። አላህ ለእናንተ ይምራል። እርሱም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነውና* አላቸው። ይህንን ቀሚሴን ይዛችሁ ሂዱ። በአባቴ ፊትም ጣሉት። የሚያይ ሆኖ ይመጣልና። ቤተሰቦቻችሁንም በሙሉ አምጡልኝ አላቸው። ግመል ጫኞችም ከግብፅ በወጡ ጊዜ አባታቸው እኔ የዩሱፍን ሽታ በእርግጥ አገኛለሁ። ባታቄሉኝ ኖሮ (ታምኑኝ ነበር አለ)። በአላህ እንምላለን አንተ በእርግጥ እስካሁንም በዚያው በቀድሞው ስህተትህ ውስጥ ነህ አሉት። አብሳሪውም በመጣ ጊዜ ቀሚሱን በፊቱ ላይ ጣለው፤ ወዲያውም የሚያይ ሆነ። እኔ ለእናንተ ከአላህ በኩል የማታውቁትን አውቃለሁ አላልኳችሁም ነበርን? አላቸው። አባታችን ሆይ፣ ለኃጢያቶቻችን ምሕረትን ለምንልን። እኛ ጥፋተኞች ነበርንና አሉ። ወደ ፊት ለእናንተ ጌታዬን ምሕረትን እለምንላችኋለሁ። እነሆ፣ እርሱ መሓሪ አዛኝ ነውና አላቸው።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አላህ በእርግጥ ርህራሄን ፈጥሯል። ርህራሄን ከፈጠረበት ዕለት ጀምሮ በአንድ መቶ ቦታዎች ከፋፍሎታል። ዘጠና ዘጠኙን ክፍሎች ከራሱ ጋር አደረጋቸውና አንዱን ክፍል ወደ ፍጡራኖቹ ላከው። አንድ አማኝ ያልሆነ ሰው በአላህ እጅ ውስጥ ያሉትን ርህራሄዎች ቢያውቁ ኖሮ ጀነት እገባለሁ የሚለውን ተስፋ አያጣም ነበር። እንዲሁም አንድ ሙእሚን አላህ ዘንድ ያለውን ቅጣቶች ቢያውቅ ኖሮ ራሱን ከእሳት የተጠበቅኩ ነኝ ብሎ አያስብም ነበር።»

فَلَمَّا دَخَلُواْ عَلَىٰ يُوسُفَ ءَاوَىٰٓ إِلَيۡهِ أَبَوَيۡهِ وَقَالَ ٱدۡخُلُواْ مِصۡرَ إِن شَآءَ ٱللَّهُ ءَامِنِينَ ﴿٩٩﴾
وَرَفَعَ أَبَوَيۡهِ عَلَى ٱلۡعَرۡشِ وَخَرُّواْ لَهُۥ سُجَّدٗاۖ وَقَالَ يَـٰٓأَبَتِ هَٰذَا تَأۡوِيلُ رُءۡيَٰيَ مِن قَبۡلُ قَدۡ
جَعَلَهَا رَبِّي حَقّٗاۖ وَقَدۡ أَحۡسَنَ بِيٓ إِذۡ أَخۡرَجَنِي مِنَ ٱلسِّجۡنِ وَجَآءَ بِكُم مِّنَ ٱلۡبَدۡوِ مِنۢ بَعۡدِ
أَن نَّزَغَ ٱلشَّيۡطَٰنُ بَيۡنِي وَبَيۡنَ إِخۡوَتِيٓۚ إِنَّ رَبِّي لَطِيفٞ لِّمَا يَشَآءُۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡحَكِيمُ ﴿١٠٠﴾

**99-100.** በዩሱፍ ላይም በገቡ ጊዜ ወላጆቹን ወደ እርሱ አስጠጋቸው በአላህም ፈቃድ ጥብቆች ስትሆኑ ምስርን (ግብጽን) ግቡ አላቸው። ወላጆቹንም በዙፋኑ ላይ አወጣቸው ለርሱም ሰጋጆች ሆነው ወረዱለት። አባቴ ሆይ!፣ ይህ ፊት ያየሁት ሕልም ፍች ነው። ጌታዬ በእርግጥ እውነት አደረገው። ከወህኒ ቤትም ባወጣኝና ሰይጣንም በእኔና በወንድሞቼ መካከል ከአበላሸ በኋላ እናንተን ከገጠር ባመጣችሁ ጊዜ በእርግጥ ለእኔ መልካም ዋለልኝ። ጌታዬ ለሚሻው ነገር እዝነቱ ረቂቅ ነው። እነሆ እርሱ አዋቂና ጥበበኛ ነው አለ።

۞ رَبِّ قَدۡ ءَاتَيۡتَنِي مِنَ ٱلۡمُلۡكِ وَعَلَّمۡتَنِي مِن تَأۡوِيلِ ٱلۡأَحَادِيثِۚ فَاطِرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ
أَنتَ وَلِيِّۦ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِۖ تَوَفَّنِي مُسۡلِمٗا وَأَلۡحِقۡنِي بِٱلصَّـٰلِحِينَ ﴿١٠١﴾

**101.** ጌታዬ ሆይ፣ ከንግስና በእርግጥ ሰጠኸኝ። ከህልሞችም ፍች አስተማርከኝ። የሰማያትና የምድር ፈጣሪ ሆይ፣ አንተ በቅርቢቱና በመጨረሻይቱ ዓለም ረዳቴ ነህ። ሙስሊም ሆኜ ግደለኝ። ወደ መልካም ሰሪዎችም አስጠጋኝ (አለ)።

ذَٰلِكَ مِنۡ أَنۢبَآءِ ٱلۡغَيۡبِ نُوحِيهِ إِلَيۡكَۖ وَمَا كُنتَ لَدَيۡهِمۡ إِذۡ أَجۡمَعُوٓاْ أَمۡرَهُمۡ وَهُمۡ يَمۡكُرُونَ ﴿١٠٢﴾
وَمَآ أَكۡثَرُ ٱلنَّاسِ وَلَوۡ حَرَصۡتَ بِمُؤۡمِنِينَ ﴿١٠٣﴾ وَمَا تَسۡـَٔلُهُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍۚ
إِنۡ هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ لِّلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٠٤﴾

**102-104.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ ወዳንተ የምናወርደው ሲሆን ከሩቅ ወሬዎች ነው። አንተም እነርሱ በዩሱፍ ላይ በሚመክሩ ሆነው ነገራቸውን በቆረጡ ጊዜ እነርሱ ዘንድ አብረህ አልነበርክም። አብዛሀኛዎቹን ሰዎች ለማመናቸው ብትጓጓም የሚያምኑ አይደሉም። (ሙሐመድ ሆይ)፣ በቁርአን ላይ ምንም ዋጋን አትጠይቃቸውም። እርሱ ለዓለማት ግሳጼ እንጂ ሌላ አይደለም።

وَكَأَيِّن مِّنْ ءَايَةٍ فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ يَمُرُّونَ عَلَيْهَا وَهُمْ عَنْهَا مُعْرِضُونَ ﴿١٠٥﴾
وَمَا يُؤْمِنُ أَكْثَرُهُم بِٱللَّهِ إِلَّا وَهُم مُّشْرِكُونَ ﴿١٠٦﴾ أَفَأَمِنُوٓا۟ أَن تَأْتِيَهُمْ غَٰشِيَةٌ مِّنْ عَذَابِ
ٱللَّهِ أَوْ تَأْتِيَهُمُ ٱلسَّاعَةُ بَغْتَةً وَهُمْ لَا يَشْعُرُونَ ﴿١٠٧﴾ قُلْ هَٰذِهِۦ سَبِيلِىٓ أَدْعُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۚ عَلَىٰ
بَصِيرَةٍ أَنَا۠ وَمَنِ ٱتَّبَعَنِى ۖ وَسُبْحَٰنَ ٱللَّهِ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٠٨﴾

**105-108.** በሰማያትና በምድር ካለችው ምልክት ብዙይቱ እነርሱ ከእርሷ ዘንጊዎች ሆነው በእርሷ ላይ ያልፋሉ። አብዛኞቻቸውም እነርሱ አጋሪዎች ሆነው እንጂ በአላህ አያምኑም። ከአላህ ቅጣት ሸፋኝ አደጋ የምትመጣባቸው ወይም ሰዓቲቱ እነርሱ የማያውቁ ሲሆኑ በድንገት የምትመጣባቸው መሆኑዋን አይፈሩምን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ መንገዴ ነው። ወደ አላህ እጠራለሁ። እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን። ጥራትም ለአላህ ይገባው። እኔም ከአጋሪዎች አይደለሁም በል።

وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ إِلَّا رِجَالًا نُّوحِىٓ إِلَيْهِم مِّنْ أَهْلِ ٱلْقُرَىٰٓ ۗ أَفَلَمْ يَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ
فَيَنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۗ وَلَدَارُ ٱلْءَاخِرَةِ خَيْرٌ لِّلَّذِينَ ٱتَّقَوْا۟ ۚ أَفَلَا
تَعْقِلُونَ ﴿١٠٩﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا ٱسْتَيْـَٔسَ ٱلرُّسُلُ وَظَنُّوٓا۟ أَنَّهُمْ قَدْ كُذِبُوا۟ جَآءَهُمْ نَصْرُنَا فَنُجِّىَ مَن
نَّشَآءُ ۖ وَلَا يُرَدُّ بَأْسُنَا عَنِ ٱلْقَوْمِ ٱلْمُجْرِمِينَ ﴿١١٠﴾

**109-110.** ከአንተ በፊትም ከከተሞች ሰዎች ወደነርሱ ራዕይ የምናወርድላቸው የሆኑን ወንዶችን እንጂ አላክንም። በምድር ላይ አይሄዱምና። የእነዚያን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ሰዎች መጨረሻ አይመለከቱምን? የመጨረሻይቱም አለም ደስታ ለተጠነቀቁት ሰዎች ሁሉ በእርግጥ የተሻለች ናት። አታውቁምን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መልዕክተኞች ተስፋ በቆረጡና እነርሱ በእርግጥ የተዋሹ መሆናቸውን በተጠራጠሩ ጊዜ እርዳታችን መጣላቸው። ከዚያ እኛ የምንፈልገው ሰው እንዲድን ተደረገ። ቅጣታችንም ከአጋሪዎቹ ህዝቦች ላይ አይመለስም።

لَقَدْ كَانَ فِي قَصَصِهِمْ عِبْرَةٌ لِّأُولِي ٱلْأَلْبَٰبِ ۗ مَا كَانَ حَدِيثًا يُفْتَرَىٰ وَلَٰكِن تَصْدِيقَ ٱلَّذِي بَيْنَ يَدَيْهِ وَتَفْصِيلَ كُلِّ شَيْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿١١١﴾

**111.** በታሪካቸው ውስጥ ለአዕምሮ ባለ ቤቶች ሁሉ በእርግጥ መገሰጫ ነበረ። ይህ ቁርኣን የሚቀጣጠፍ ወሬ አይደለም። ይልቁንም ያንን በስተፊቱ ያለውን አረጋጋጭ፤ ሁሉን ጉዳዮች ገላጭና ለሚያምኑ ህዝቦችም ሁሉ መሪና፤ ችሮታ ነው።

**ከዩሱፍ ምዕራፍ ከ (1-111) ካሉ አናቅፅ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች፡-**

1. ቁርኣን ተአምራዊ የሆነ ከአላህ የተወረደ መፅሐፍ ስለ መሆኑ፡-
2. ቁርኣን በአረብኛ ቋንቋ የወረደበት የራሱ የሆነ ምክንያት እንዳለው አላህ ማረጋገጡን፤
3. ቁርኣን ብዙ ቁም ነገር አዘል ታሪኮችን አካትቶ የያዘ መፅሐፍ በመሆኑ ሌላ አፈታሪኮችን ይዞ መጓዝና ያልተረጋገጡ ታሪኮችን ለማዳመጥም መሞከሩ ተገቢ አለመሆኑን፤
4. የነብዩ (ﷺ) ነብይነት በጠንካራ ማስረጃ የተረጋገጠ ስለመሆኑ፤
5. የአላህ መልዕክተኛ ከአላህ የተላከ ነብይ መሆናቸውን ከሚያረጋግጡ እውነታዎች አንዱ ይህን ረጅምና በቀድሞ መፅሐፍት ውስጥ ያሉ ታሪኮችን በትክክል መተረካቸውና ይህንንም ያደረጉት አንድም ትምህርት ሳይኖራቸው መሆኑን፤
6. የነብዩ ዩሱፍ ታሪክ እጅግ ውብና ማራኪ በግልፅና በሚጥም መልኩ የተቀናበረ ሲሆን በውስጡም ብዙ ተለዋዋጭ ክስተቶች ማለትም፤ ከችግር ወደ ችግር፤ ከችግር ወደ ድሎት፤ ከውርደት ወደ ሹመት፤ ከባርነት ወደ ልቅና፤ ከመበታተን ወደ መሰባሰብ፤ ከመጣላት ወደ መታረቅ፤ ከሐዘን ወደ ደስታ፤ ከረሀብ ወደ ጥጋብ፤ ከክህደት ወደ እምነት መቀያየር የታየበት አስደናቂ ታሪክ ነው።
7. ዩሱፍ ታሪኩ ብቻ ሳይሆን ራሱም ውብ እንደነበር፤
8. የግብፅ ሴቶች"መላዕክት ሲሉ አድንቀውታል በጊዜውም ዩሱፍ ሕጻን ይሁን እንጂ ታማኝና ከአባቱ ዘንድ ተወዳጅ የነበረ ስለመሆኑ፤
9. አባቱ ሕልሙን ሲሰሙ ልጁ ትላቅ እንደሚሆን ተሰማቸው። የሕልም ፍች በታሪኩ ውስጥ ቀስ በቀስ እየተገለፀ መሄዱን፤
10. በህልም የሚታዩ ነገሮች በሙሉ በእውነታው ዓለም ሊንፀባረቁ እንደሚችሉና በህልም የሚታዩ ነገሮች በቶሎ በእውነታው ዓለም ሕይወት ላይ ባይከሰቱም እንኳን ዘግይተው ሊከሰቱ እንደሚችሉ፤
11. ማንኛውም ነገር ሲፈፀም በጥንቃቄ ከሆነ የሚኖረውን ከፍተኛ ፋይዳ፤
12. አባት ልጁን መንከባከብ እንዳለበት፤
13. አላህ የሰጠንን ፀጋ በሚስጥር መያዝ አስፈላጊ መሆኑንና የአላህን ፀጋ ማውሳት ይወደዳል ማለት ለአደጋ በማያጋልጥበት ሁኔታ መሆኑን፤
14. በልጆች መካከል አንዱን ከፍ አንዱን ዝቅ በማድረግ ማዳላት በመሀከላቸው ልዩነቶች እንዲፈጥሩ የሚያደርግ በመሆኑ አግባብ እንዳልሆነ፤ ሊለይ የሚገባው እንኳን ቢኖር በግልፅ መደረግ እንደሌለበት፤
15. የምቀኝነት ባህሪ የተወገዘና ለአያሌ ችግሮች ምክንያት ሊሆን የሚችል መጥፎ ስነ ምግባር መሆኑን፤

16. ሁለት አስገዳጅና ሊፈፀሙ የሚገቡ ሁኔታዎች ሲከሰቱና አንዱን የመፈፀም ግዳጅ ቢጣልብን አነስተኛ ችግር የሚያስከትለውን በመምረጥ መስራት ከኢኮኖሚያዊ ሕግጋት እንደሚመደብ፤
17. በአባትና በእናት የሚገናኙ ወንድማማቾች ከሁለት በአንድ ብቻ ከሚገናኙ ወንድማማቾች የበለጠ እንደሚተዛዘኑ፤
18. አንድ ሙስሊም አንዳንድ ጊዜ ከፍተኛ የሚባሉ ታላላቅ ወንጀሎችንም ሊዳፈር የሚችልበት ሁኔታ እንደሚኖር፤
19. አላህ ለነብዩ ዩሱፍ ታላቅ ውለታን መዋሉን፤
20. ነብዩ ዩሱፍ ከአላህ ይቅርታን ለመጠየቅ ሌሊትን መምረጣቸውን፤
21. ትዕግስት ምን ያህል ማዕረግና ክብር እንዳለውና ከአላህ እንደሚሰጥ፤
22. ቢጣልብን በደስታ የሚያስፈነድቁ ነገሮች ሲከሰቱ የደስታ ስሜትን ማሳደርና ሐሴት ማድረግ የተፈቀደ ስለ መሆኑ፤
23. አላህ ለባሪያዎቹና ለቅን አገልጋዩቹ ክብርን እንደሚያጎናፅፍ ይህንንም በተግባር እንደሚያሳይ፤
24. የሴቶች ተንኮል ከባድና ረቂቅ ስለመሆኑ፤
25. አቅም በፈቀደ መጠን የሰውን ነውር መደበቅና ነውሩን ከማጋለጥም መቆጠብ የሚገባ መሆኑን፤
26. አላህን ለማሸነፍ የሚሞክርና ከአላህ ጋር የሚታገል ሰው ተሸናፊ መሆኑ የማይቀር ስለመሆኑ፤
27. መልካም ምንዳ ለማግኘት ጥሩ የሆነ ንያ ወሳኝ ሚና እንዳለው፤
28. ሰው ሁሉም ነገርን መረዳትና ማወቅ የሚፈልግ ስለመሆኑ፤
29. ሰው የራሱን ክብር ለማስጠበቅ እንደሚንቀሳቀስ ይህም ለራሱ ክብር ከመጨነቁ የተነሳ እንደሆነና ክብሩን የተዳፈረን አካል ለመበቀል እንደሚያደባ፤
30. ዩሱፍ ወንጀል ሰርተው አላህን ከማስቀየም ይልቅ የእስር ቅጣት መቅመስ መምረጣቸውን፤
31. አላህን ያለማወቅ የወንጀሎች ሁሉ ዋነኛ ምክንያት ስለመሆኑ፤
32. የዩሱፍ እስር ቤት መግባት ቅጣት ቢመስልም ለእርሳቸው ግን ብርሃንን ያጎናፀፋቸው መሆኑን፤
33. በእስር መቀጣት ብቻውን ታሣሪውን ወንጀለኛ እንደማያደርገውና ንፁሃንም ያለምንም ወንጀል ሊታሰሩ የሚችሉበት አጋጣሚ እንደሚከሰት፤
34. ለዳዕዋ አመች የሆኑ ዘዴዎችን በሙሉ በመጠቀም ዳዕዋን ማስፋፋት የሚመረጥ ስለመሆኑ፤
35. ራስን ከሽርክ ተግባራትና ከሙሽሪኮች ጋር ከሚመሠረት ወዳጅነት መጠበቅ እንደሚገባና ይህም ግዴታ ስለመሆኑ፤
36. አያት እንደ ወላጅ አባት ቅርብ መሆኑን፤
37. የቀደምት ህዝቦችን ታሪክ በማንበብ በመማር የተውሒድን ፅንስ ሃሳብ ማወቅ እንደሚቻል፤
38. እውነት ተብሎ የሚጠራው አላህ እውነት ነው ብሎ ያስቀመጠው ነገር መሆኑንና በአንፃሩም ውሸት ተብሎ የሚጠራውም እንዲሁ አላህ ውሸት ብሎ የሰየመው ነገር እንደሆነ፤
39. በማንኛውም ርዕስ ዕውቀት ለማግኘትና ምላሽ የሚያሻቸው ችግሮች ሲከሰቱ አዋቂዎችን መጠየቁ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
40. ነብዩ ዩሱፍ አላህን በመዘንጋት ለንጉሱ ከእስር ቤት እንዲያወጣቸው አስታዋሽ ሰው ልከው እንደነበር፤
41. ከሃዲ ትክክለኛና በእውነተኛው ዓለም ሊንፀባረቅ የሚችል ሕልም ሊመለከት እንደሚችል፤ ህልም ሁለት ዓይነት እንደሆነ ይኼውም ሰይጣናዊ ሕልምና መንፈሳዊ እውነተኛ ህልም ተብሎ እንደሚታወቅ፤
42. መርሣት የሰዎች ባህርይ መሆኑና ሰው ሁልጊዜም ያለፈውን የሚረሳ ፍጡር መሆኑን፤

43. ሰዎን መልካምን ሲሰሩ በተገቢው መልኩ ማወደስና ማሞገስ የማይከለከል መሆኑንና እውቀት ታላቅ ማዕረግን የሚያሰጥ መሆኑንና ነብዩ ዩሱፍ በእውቀታቸው ምክንያት ትልቅ ቦታ እንዳገኙ፤
44. ትዕግስትና ችሎታ ለስኬታማነት አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
45. እውነትን መናገር ሐቅን የሙጥኝ ብሎ መያዝ የሚያኮራ ተግባር ስለመሆኑ፤
46. ራስን መውቀስና ሁኔታዎች መጠራጠር ተገቢ መሆኑን፤
47. ማንኛውንም ስራ የሚሰራ ሰው አሣምሮና ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያለበት ስለ መሆኑ፤
48. ነቢዩላህ ዩሱፍን በመሾምና ታላቅነታቸውን ለህዝቡ በማሳወቅ ረገድ አላህ ትልቅ ተአምር ማሳየቱን፤
49. ነብዩ ዩሱፍ ወንድማቸውን ለማግኘት የተጠቀሙት ዘዴ ረቂቅ እንደነበረ፤
50. እምነት በሰዎች ላይ ከፍተኛ የባህርይ ለውጥ የሚያመጣና መልካም ስብዕናን የሚያላብስ መሆኑን፤
51. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በአላህ ስም መማል የተፈቀደ ስለመሆኑ፤
52. በራስ ላይ አሉባልተኞች የሚያስወሩት አሉባልታና የሚያደርሰውን አደጋ ለመከላከል እንቅስቃሴ ማድረግ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
53. ነቢዩላህ ዩሱፍ ጊዜ በሌብነት ወንጀል በተከሰሰና ሌብነቱ በተረጋገጠበት ወንጀለኛ ላይ ይወሰድ የነበረው ሸሪአዊ ቅጣት ምን ይመስል እንደነበረ ቁርአን ማስተማሩንና በወቅቱ የግብፅ መንግስት ሌባን በምን አይነት መልኩ ይቀጣ እንደነበርም መገለፁ፤
54. ነብዩ የዕቆብ በአላህ ላይ በእጅጉ ይመኩ እንደነበርና ተወኩላቸውም ጠንካራ የነበረ መሆኑን፤
55. ከቅርብ ዘመድ ጋርም ቢሆን ቃልኪዳን መግባት እንደሚቻል፤
56. አይንናስ ሐቅ መሆኑንና ሰዎች በዐይንናስ ከሚደርስ አደጋ ራሳቸውን መጠበቅ እንደሚገባቸው፤
57. ለማንኛውም ነገር በአላህ መወከል እንደሚገባ፤
58. ከሰዎች ውስጥ ብዙዎቹ ትክክለኛውን ነገር የማያውቁ መሆናቸው በቁርአን መረጋገጡ፤
59. ነብዩ ዩሱፍ ወንድማቸውን ለመለየት በማሰብ ከቡድኑ እንዴት ለይተው ወደ ኋላ እንዳስቀሩት፤
60. መልካም ውለታን ለዋለልን ሰው ካባ መሸለምና በስጦታ ማበርከትም የሚፈቀድ ስለመሆኑ፤
61. ለአንድ ሰው ዋስ መሆንና የሚፈለግበት ጉዳይ ተጣርቶ ነፃ እስከሚሆን ዋስትና መስጠት የተፈቀደ ስለመሆኑ፤
62. ከስህተት ተመልሶ ኃጢአትን አምኖ ከአላህ ይቅርታን መጠየቅ ተገቢ ስለመሆኑ፤
63. ሰው ምንም ያህል ትዕግስተኛ ቢሆንም በመጥፎ ሰዎች ግፊትና ተንኮል መጥፎ ነገር ሊናገር እንደሚችል፤
64. ባለጉዳይ ኃላፊዎች ዘንድ ጉዳዩን ለማስፈፀም በሚሄድ ጊዜ አስተዛዝኖ ጉዳዩን ማስረዳቱ አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
65. ወንጀለኛውን ትቶ ከጉዳዩ ጋር ንክኪ የሌለውን ሌላ ሰው መጠየቅና መቅጣቱ የተከለከለ ስለመሆኑ፤
66. አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ገለል ብሎ ሚስጢራዊ ውይይት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑና ባጠቃላይ ምክክር ያለውን ጠቀሜታ፤
67. ቃልኪዳንን ማስታወስና ለመፈፀም መሞከር ተገቢ ስለመሆኑ፤
68. አንዳንድ ሰዎች በአይናፋርነታቸው ምክንያት ብዙ መልካም ነገሮች ሊያመልጣቸው እንደሚችሉና ከብዙ መልካም ነገሮችም ሊገድቧቸው እንደሚችሉ፤

69. ማንኛውም ሰው በቀድሞ ሕይወቱ ካሣለፋቸው ሁኔታዎች በመነሳት ምንም እንኳን ንፁህ የሆነ ሰው ቢሆንም መጠራጠር የተፈቀደ መሆኑን፤
70. ችግርና ብሶትን ለአላህ በስሞታ ማቅረብ እንደሚቻል፤
71. ከልብ ውስጥ ጠልቆ የሚገባ ከባድ ሀዘን ለበሽታ ወይም ለሞት የሚዳርግ ስለመሆኑ፤
72. ተስፋ መቁረጥ የተከለከለ መሆኑን፤
73. ችግርን ለማስረዳት በማሰብ የተከሰቱ ችግሮችን ለሰዎች መናገር እንደሚቻል፤
74. ወንጀልን መዳፈር የሚከሰተው አላህን በተገቢው መልኩ ካለማወቅ እንደሆነ፤
75. በደልን ይቅር ማለትና አጥፊን በይቅርታ ማለፍ ያለው ምንዳ ከፍተኛ መሆኑን፤
76. የነብዩ ዩሱፍን የገላ ጠረን ይዛ የመጣችን ንፋስ በማስነሳት ለአባታቸው የዕቁብ በማሽተት ረገድ አላህ ያሳየውን ተአምርና ለብዙ ዓመታት ታውሮ የነበረውን የነቢዩ ያዕቆብ አይን በማብራትም ያሳየውን ተዐምር፤
77. ነብዩ የዕቁብ የነበራቸውን ጥልቅ ትዕግስትና የተላበሱትን ይቅርታ ባይነት፤
78. ታላላቅ ሰዎችን ከከተማ ወጣ ብሎ ወይም ወደ ሚመጡበት ጎዳና ቀረብ ብሎ ለመቀበል ጉዞ ማድረግ እንደሚፈቀድ፤
79. ነብዩ ዩሱፍ በታዳጊነታቸው ያዩት ህልም ከብዙ ዓመታት በኋላ ተፈፃሚ መሆኑንና ይህም ህልም ተፈፃሚ ለመሆን አንዳንድ ጊዜ ረጅም አመታት ሊወስድና ሊዘገይ እንደሚችል፤
80. ከምድራዊ ሕይወት ወከባዎች ራቅ ብሎና ጊዜ ወስዶ በዕርጋታና በፀጥታ አኼራን ማስታወስ ያለውን ተፈላጊነት፤
81. አላህን እና መልካም ጓደኞችን መናፈቅ ተገቢ ስለመሆኑ፤
82. በህመምና በምድራዊ ስቃይ በመሰላቸት ሳይሆን ጀነት በመናፈቅ ሞትን መመኘት እንደሚገባ፤
83. ኢስላማዊ ትምህርቶችን የሃይማኖትን ድንጋጌዎች ለህዝቦች በነፃ ማዳረስ ግዴታ ስለ መሆኑ፤ ዝንጉነትና የአላህን ፍጡራን በመመልከት አለማስተንተን የተወገዘ ተግባር መሆኑን፤
84. ብዙ ሰዎች አመንን ቢሉም እምነታቸው ከሽርክ ሙሉ በሙሉ የፀዳ አለመሆኑንና የሽርክ ተግባር ሌሎችንም ወንጀሎች ሊያስከትል የሚችል አደጋው እጅግ የከፋ ስለ መሆኑ፤
85. ሙቀ መነካትና ዳግሞ ሕይወት እንዳለ ማመንና ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ፤
86. ነብዩን (ﷺ) እወደዋለሁ የሚል አማኝ በሙሉ ዳዕዋ የማድረግ ግዴታ ያለበት ስለ መሆኑ፤
87. አስተማሪ የሆነ በቅድሚያ ስለሚያስተምረው ነገር እርግጠኛ መሆን እንደሚገባው፤
88. አላህን አንድ አድርጎ ለብቻው ማምለክ የሚገባው መሆኑን፤
89. የነብይነት ማዕረግ የሚሰጠው ለወንዶች ብቻ መሆኑን፤
90. የተውሒድ ጥቅም በምድራዊ ሕይወትም ሆነ በአኼራ ላይ ጎልቶ የሚታይ ስለመሆኑ፤
91. አላህ ለቅን አገልጋይ ባሪያዎቹ ድልን ሊያዘገይባቸው እንደሚችል፤
92. በቁርኣን ትምህርት የሚጠቀሙት አማኞች ብቻ ስለመሆናቸው፤
93. ለመጥፎ ነገሮች ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች አቅም በፈቀደ ያህል መራቅ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
94. ፍትሃዊነት በሁሉም ነገር ላይ አስፈላጊ መሆኑን፤
95. የሰው ልጅ የሚታየው የመጨረሻው ሁኔታው እንጂ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ከታሪኩ በግልፅ መማር፤
96. አላህ ለነብዩ ዩሱፍ ከሰጣቸው እውቀትና ጥሩ ስነ ምግባር ቻይነትና ይቅርባይነትን መመልከት፤
97. የነብዩ ዩሱፍ ወንድሞች ዩሱፍን ከመግደል ይልቅ ዋሻ ውስጥ መጣልን ለምን እንደመረጡ፤

98. ፊትና ሊያመጣ በሚችል መልኩ ከባዕድ ሴት ጋር አብሮ ከመገለል መጠንቀቅ፤
99. ምልክቶች፡ ተመሳሳይ ነገሮችን መለየት በሚያስቸግርበት ጊዜ አንዱን ከሌላው ለመለየት እንደሚጠቅሙ፤
100. እውቀትና አዕምሮ የሰውን ልጅ ወደ መልካም እንደሚጠሩት ሁሉ አለማወቅ ደግሞ ለመጥፎ እንደሚጋብዝ፤
101. አላህን መገዛት በደስታ ቀን ብቻ ሳይሆን በችግርም ቀን መሆን እንዳለበት፤
102. ማንም ሰው ለሚሰራው ስራ ቅደም ተከተሉን እንደ አስፈላጊነቱ ማከታተል ሲኖርበት በጣም የሚያስፈልገውን ትቶ ተራ ነገርን ለጠየቀ ለጥያቄው መልስ ከመስጠት በፊት ያን በጣም የሚያስፈልገውን ማስተማሩ የአስተማሪውን ታትሪነትና አሳቢነት እንደሚያመለክት፤
103. በእውቀት ተጠያቂ የሆነ ሰው ጠያቂውን የሚጠቅመውን ነገር ሁሉ መጠቆም እንዳለበት፤
104. ሰዎች የራሳቸውን ባህሪ ለሰው መናገር ችግር እንደሌለው፤
105. አላህ ቸርነቱን ለፈለገው ሰው እንደፈለገው መስጠት እንደሚችል፤
106. ነቢዩላህ ዩሱፍ የነበራቸው የማስተዳደር ከፍተኛ ብቃትና ችሎታ በግልፅ መመልከት፤
107. እንግዳን ማስተናገድ በኢስላም ተገቢ መሆኑን፤
108. አንዱ በሌላው ላይ መጥፎ ጥርጣሬን ማሳደር ግልፅ ምልክት እስከሌለው ድረስ ክልክል መሆኑን፤
109. አይንናስን ለመከላከል የሚያስችሉ ምክንያቶችን መጠቀም በኢስላም እንደሚቻል፤
110. የራስን መብት ለማስመለስ ዘዴዎችን መጠቀም እንደሚፈቀድ፤
111. የሰው ልጅ በሚያውቀው ብቻ መመስከር እንዳለበት፤
112. የሰው ልጅ ሁልጊዜም እምነቱን እንዲያፀናለት አላህን መለማመጥና መማፀን እንዳለበት፤
113. አላህ ለነብዩ ዩሱፍ የዋለላቸው ጸጋና በኋላ የደረሱበት ከፍተኛ ማዕረግ ምን ይመስል እንደነበር እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የዩሱፍ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (13)
# የነጎድጓድ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልረዕድ)

سُورَةُ الرَّعۡدِ

## የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ (43) ናቸው።
## የሱረቱ አርረዕድ መግቢያ

ከአጀማመሩ የቁርኣንን ትልቅነት ያስታውሳል። ቁርኣን ከአላህ እንደመጣም በግልጽ ያውጃል። ከዚያ በመፍጠር ላይ ያለውን አቅሙን በመግለፅ መመለስንም ማለትም ከሞት በኋላ መቀስቀስ እንደሚችል አላህ ሁሉን የሚያውቅ በዚህች ዓለምም የሚቀጣ በመሆኑ የአኼራውም ከዚሁ አንጻር መታየት እንደሚገባው ያመለክታል።

ሰማይ ለሁሉም ሰዎች እይታ የተመቻቸ ነው። ትንሽ ትልቅ ሴት ወንድ ሳይባል ሁሉም ያዩታል። ውበቱን፣ ግዝፈቱን፣ ዓይን ሊያየው የሚችል አዕማድ እንዳላቀመው ሁሉ ማየት ይችላል። ከአላህ ውጭ በዚህ መልኩ ሰማይን ያቆመውና ያነፀው የለም። የሰው ልጅ ይህን አስተውሎ ለፈጣሪው እውቅና እንዲሰጥ ጥሪውን ይጋብዛል። ዕፅዋት ወንዴና ሴቴ ፆታ እንዳሏቸው የሰው ልጅ የደረሰበት አሁን ነው። በቅርቡ። ከዚህ ክፍለ ዘመን በፊት ይህ አይታወቅም ነበር። ቁርኣን ግን ይህን እውነታ ቀድሞ አውጇል። የሰማያትንና የምድርን ምስጢር ሁሉ ዐዋቂ የሆነው አምላክ ድርሳን ነውና።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓرۚ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِۗ وَٱلَّذِيٓ أُنزِلَ إِلَيۡكَ مِن رَّبِّكَ ٱلۡحَقُّ
وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يُؤۡمِنُونَ ١

**1.** አሊፍ ላም ሚይም ራ፤* (በእነዚህ ፊደሎች ምን እንደፈለገ አላህ ራሱ ብቻ ያውቃል)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚህ አናቅጽ ከመጽሐፉ አንቀፆች መካከል ናቸው። ያም ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደው እውነት ነው። ግን አብዛኛዎቹ ሰዎች አያምኑም።

✶ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

ٱللَّهُ ٱلَّذِي رَفَعَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ بِغَيۡرِ عَمَدٖ تَرَوۡنَهَاۖ ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ وَسَخَّرَ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ
كُلّٞ يَجۡرِي لِأَجَلٖ مُّسَمّٗىۚ يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَ يُفَصِّلُ ٱلۡأٓيَٰتِ لَعَلَّكُم بِلِقَآءِ رَبِّكُمۡ تُوقِنُونَ ٢

**2.** አላህ ያ ሰማያትን የምታይዋት (ቋሚዎች) አዕማድ ሳይኖራት በችሎታው ከፍ ያረጋት፤ ከዚያ በዐርሹ ላይ ከፍ አለ*። ፀሐይንና ጨረቃን የገራ ነው። ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ። ነገሩን ሁሉ ያስተናብራል። ከጌታችሁ መገናኘትን ታረጋግጡ ዘንድ ተአምራቶችን ይዘረዝራል።

✶ ይህን አይነቱን. በምን መልኩ መረዳት እንደሚገባን በሱረቱ አል አዕራፍ. (54) ኛው አንቀፅ ግርጌ በስፊው አልፏልና ተመለከተው።

وَهُوَ ٱلَّذِي مَدَّ ٱلۡأَرۡضَ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَٰسِيَ وَأَنۡهَٰرٗاۖ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ جَعَلَ فِيهَا زَوۡجَيۡنِ
ٱثۡنَيۡنِۖ يُغۡشِي ٱلَّيۡلَ ٱلنَّهَارَۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٣

**3.** እርሱ ያ፣ (አላህ) ምድርን የዘረጋ፤ በእርሷም ውስጥ ተራራዎችንና ወንዞችን ያደረገ። በውስጧም ከፍሬዎች ሁሉ ሁለት ሁለት* ዓይነቶችን ያደረገ ነው። ሌሊትን በቀን ይሸፍናል። በዚህም ውስጥ ለሚያስተነትኑ ህዝቦች ሁሉ ብዙ ምልክቶች አሉ።

✶ ይህ አባባል "መንታዎች የሆኑም መንታዎች ያልሆኑም" ተብሎ ተተርጉሟል። የሚመሳሰሉና የማይመሳሰሉ የሚል ፍችም አላቸው። ኢብኑ ዐባስ "ሲንዋን" ሁለት ራስ አንድ ሥር ያላት የተምር ዛፍ ነች። ብለዋል።

وَفِي ٱلۡأَرۡضِ قِطَعٞ مُّتَجَٰوِرَٰتٞ وَجَنَّٰتٞ مِّنۡ أَعۡنَٰبٖ وَزَرۡعٞ وَنَخِيلٞ صِنۡوَانٞ وَغَيۡرُ صِنۡوَانٖ يُسۡقَىٰ
بِمَآءٖ وَٰحِدٖ وَنُفَضِّلُ بَعۡضَهَا عَلَىٰ بَعۡضٖ فِي ٱلۡأُكُلِۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ٤

4. በምድር ውስጥ የተጎራበቱ ቁርጥራጮች አሉ። የወይኖች አትክልቶችም፤ አዝርዕቶችም መንታዎችና መንታዎች ያልኾኑ ዘንባባዎች አሉ። በአንድ ውሃ ይጠጣሉ። በጣዕም ግን ይለያያሉ ከፊልዋንም በከፊሉ ላይ በሚበላው ሰብል እናበልጣለን። በዚህም ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች ሁሉ ብዙ ተአምራት አለበት።

۞ وَإِن تَعۡجَبۡ فَعَجَبٞ قَوۡلُهُمۡ أَءِذَا كُنَّا تُرَٰبًا أَءِنَّا لَفِي خَلۡقٖ جَدِيدٍۗ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ
بِرَبِّهِمۡۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ ٱلۡأَغۡلَٰلُ فِيٓ أَعۡنَاقِهِمۡۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ٥

5. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ብትደነቅም አፈር በኾንን ጊዜ እኛ አዲስ ፍጥረት እንሆናለን? ማለታቸው በጣም የሚደንቅ ነው። እነዚህ ሰዎች ማለት እነዚያ በጌታቸው የካዱት ሰዎች ናቸው። (ያለማመናቸው ምሳሌ) እነዚህም እንዛዝላዎች በአንገቶቻቸው ላይ ያሉባቸው ናቸው። እነዚህም የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው።

وَيَسۡتَعۡجِلُونَكَ بِٱلسَّيِّئَةِ قَبۡلَ ٱلۡحَسَنَةِ وَقَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهِمُ ٱلۡمَثُلَٰتُۗ وَإِنَّ رَبَّكَ لَذُو
مَغۡفِرَةٖ لِّلنَّاسِ عَلَىٰ ظُلۡمِهِمۡۖ وَإِنَّ رَبَّكَ لَشَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ٦

6. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ በፊት የመሰሎቻቸው ቅጣቶች በእርግጥ ያለፉ ሲኾኑ ከመልካሙ በፊት በመጥፎ ያስቸኩሉሃል ጌታህ ለሰዎች ሁሉ ከመበደላቸው ጋር በእርግጥ የምህረት ባለቤት ነው። ጌታህ በእርግጥ ቅጣቱ ብርቱ ነው።

وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَوۡلَآ أُنزِلَ عَلَيۡهِ ءَايَةٞ مِّن رَّبِّهِۦٓۗ إِنَّمَآ أَنتَ مُنذِرٞۖ وَلِكُلِّ قَوۡمٍ هَادٍ ٧

7. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች በእርሱ ላይ ከጌታው ተአምር ለምን አልተወረደለትም ይላሉ። አንተ አስፈራሪ ብቻ ነህ ለሕዝብም ሁሉ መሪ አለላቸው።

ٱللَّهُ يَعۡلَمُ مَا تَحۡمِلُ كُلُّ أُنثَىٰ وَمَا تَغِيضُ ٱلۡأَرۡحَامُ وَمَا تَزۡدَادُۚ وَكُلُّ شَيۡءٍ عِندَهُۥ بِمِقۡدَارٍ ٨
عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ ٱلۡكَبِيرُ ٱلۡمُتَعَالِ ٩

**8-9.** አላህ ሴት ሁሉ የምታረግዘውን ፅንስ ሁሉ ጠንቅቆ ያውቃል። ማሕፀኖች የሚያጎድሉትንም ሆነ የሚጨምሩትን ያውቃል። ነገሩ ሁሉ እርሱ ዘንድ በልክ የተወሰነ ነውና። ሩቁንና ቅርቡን ዐዋቂ የሆነ ታላቅና የላቀ ጌታ ነው።

سَوَآءٞ مِّنكُم مَّنۡ أَسَرَّ ٱلۡقَوۡلَ وَمَن جَهَرَ بِهِۦ وَمَنۡ هُوَ مُسۡتَخۡفِۭ بِٱلَّيۡلِ وَسَارِبُۢ
بِٱلنَّهَارِ ١٠ لَهُۥ مُعَقِّبَٰتٞ مِّنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَمِنۡ خَلۡفِهِۦ يَحۡفَظُونَهُۥ مِنۡ أَمۡرِ ٱللَّهِۗ
إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُغَيِّرُ مَا بِقَوۡمٍ حَتَّىٰ يُغَيِّرُواْ مَا بِأَنفُسِهِمۡۗ وَإِذَآ أَرَادَ ٱللَّهُ بِقَوۡمٖ سُوٓءٗا
فَلَا مَرَدَّ لَهُۥۚ وَمَا لَهُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَالٍ ١١

**10-11.** ከናንተ ውስጥ ቃሉን ዝቅ ያደረገ ሰው በእርሱ የጮኸም ሰው እርሱ በሌሊት ተደባቂም በቀን ተገልፆ ኺያጅም የኾነ ሰው (እርሱ አላህ ዘንድ) እኩል ነው (አላህ ያውቀዋል)። ለእርሱ ለሰው በስተፊቱም ከኋላውም በአላህ ትዕዛዝ ከክፋ የሚጠብቁት ተተካኪዎች መላዕክት አሉት። አላህ በሕዝቦች ዘንድ ያለውን ጸጋ በነፍሶቻቸው ያለውን (ሁኔታ) እስከሚለውጡ ድረስ አይለውጥም። አላህም በሰዎች ላይ ክፉን በሻ ጊዜ ለእርሱ መመለስ የለውም። ለእነርሱም ከእርሱ ሌላ ምንም ተከላካይ የላቸውም።

هُوَ ٱلَّذِي يُرِيكُمُ ٱلۡبَرۡقَ خَوۡفٗا وَطَمَعٗا وَيُنشِئُ ٱلسَّحَابَ ٱلثِّقَالَ ١٢ وَيُسَبِّحُ ٱلرَّعۡدُ
بِحَمۡدِهِۦ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ مِنۡ خِيفَتِهِۦ وَيُرۡسِلُ ٱلصَّوَٰعِقَ فَيُصِيبُ بِهَا مَن يَشَآءُ وَهُمۡ يُجَٰدِلُونَ
فِي ٱللَّهِ وَهُوَ شَدِيدُ ٱلۡمِحَالِ ١٣

**12-13.** እርሱ ያ፣ የምትፈሩና የምትከጅሉም ስትኾኑ ብልጭታን የሚያሳያችሁ ከባዶች ደመናዎችንም የሚያስገኝ ነው። ነጎድጓድ አላህን በማመስገን ያጠራል። መላዕክትም እርሱን ለመፍራት ያጠሩታል መብረቆችንም ይልካል። እነርሱም ከሐዲያን በአላህ የሚከራከሩ ሲኾኑ በእርሷ የሚሻውን ሰው ይመታል እርሱም ሀይለ ብርቱ ነው።

ከነጎድጓድ ምዕራፍ ከ (8-13) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ አሚር ኢብኑ ጡፈይልና አርበድ ኢብኑ ቀይስ የተባሉ ግለሰቦች ነብዩን (ﷺ) ለማግኘት ወደ መዲና በማምራት ላይ ሳሉ ከሱሃቦች አንዱ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አሚር ኢብኑ ጡፈይል ወደ እርስዎ እየመጣ ነው» አላቸው። ነብዩም (ﷺ) «ተውት ይምጣ አላህ ኸይር ከሻለት ቀናውን መንገድ ይመራዋል» በሚል ፈቀዱለትና ወደ እሳቸው ሲደርስ «ሙሐመድ ሆይ! ከሰለምኩኝ ለእኔ ምን ታደርግልኛለህ» አላቸው። እሳቸውም «ለሁሉም ሙስሊሞች ያላቸው መብት አለህ። አላህ በሁሉም መስሊሞች ላይ የተደነገገው ግዴታ ሁሉ አለብህ አሉት።» አሚርም «ከአንተ በኋላ ስልጣኑ ለእኔ እንዲሆን ፈቃደኛ ነህን» አላቸው። ነብዩም (ﷺ) «ፈፅሞ የዚህ ጉዳይ በእኔ አይደለም። አላህ ነው ለፈለገው የሚሰጠው» አሉ።

በዚህ ጊዜ አሚር ለጓደኛው ለአርበድ «እኔ በወሬ ስይዝልህ አንገቱን በለው» በማለት መከረው። ከዚያም ወደ ነብዩ (ﷺ) ሄዱና አርበድ ከነብዩ ጀርባ ሁኖ ከተመቻቸ በኋላ ጎራዴውን ስንዝር ያህል እንዳወጣው እጁ ላይ ደርቆ ቀረ። ነብዩም (ﷺ) ወደ እሱ ዘወር ሲሉ ተግባሩን ተመለከቱ። በዚህ ጊዜ «ጌታዬ ሆይ! በፈለከው አይነት ከእኒህ ሰዎች ተንከል አድነኝ» ብለው ለመኑ። ከዚያም አላህ በአርበድ ላይ መብረቅ ልኮ አቃጠለው። አሚርም ለጊዜው በነብዩ (ﷺ) ላይ እየዛተ ሸሸ። ሆኖም ግን አላህ ወዲያውኑ ተበቀለው። ምክንያቱም በመንገድ ላይ እንዳለ ፈረሱ ላይ ሞተ።

لَهُۥ دَعۡوَةُ ٱلۡحَقِّۚ وَٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ لَا يَسۡتَجِيبُونَ لَهُم بِشَيۡءٍ إِلَّا كَبَٰسِطِ كَفَّيۡهِ
إِلَى ٱلۡمَآءِ لِيَبۡلُغَ فَاهُ وَمَا هُوَ بِبَٰلِغِهِۦۚ وَمَا دُعَآءُ ٱلۡكَٰفِرِينَ إِلَّا فِي ضَلَٰلٖ ١٤

**14.** ለርሱም (ለአላህ) የእውነት መጠሪያ አለው። እነዚያ ከእርሱ ሌላ የሚገዟቸው ጣዖታት ወደ አፉ ይደርስ ዘንድ ወደ ውሃ መዳፎቹን በሩቅ ኾኖ እንደሚዘረጋ (ሰው መልስ) እንጂ በእነርሱ በምንም አይመልሱላቸውም። እርሱም ወደ አፉ ደራሽ አይደለም። የከሓዲያን ጥሪ ከንቱ እንጂ ሌላ አይደለም።

وَلِلَّهِ يَسۡجُدُ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ طَوۡعٗا وَكَرۡهٗا وَظِلَٰلُهُم بِٱلۡغُدُوِّ وَٱلۡأٓصَالِ۩ ١٥

**15.** በሰማያትና በምድር ያሉት ሁሉ በውድም ኾነ በግድ ለአላህ ይሰግዳሉ። ጥላዎቻቸውም በጧቶችና በማታዎች ይሰግዳሉ።

قُلۡ مَن رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ قُلِ ٱللَّهُۚ قُلۡ أَفَٱتَّخَذۡتُم مِّن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ لَا يَمۡلِكُونَ
لِأَنفُسِهِمۡ نَفۡعٗا وَلَا ضَرّٗاۚ قُلۡ هَلۡ يَسۡتَوِي ٱلۡأَعۡمَىٰ وَٱلۡبَصِيرُ أَمۡ هَلۡ تَسۡتَوِي ٱلظُّلُمَٰتُ
وَٱلنُّورُۗ أَمۡ جَعَلُواْ لِلَّهِ شُرَكَآءَ خَلَقُواْ كَخَلۡقِهِۦ فَتَشَٰبَهَ ٱلۡخَلۡقُ عَلَيۡهِمۡۚ قُلِ ٱللَّهُ خَٰلِقُ كُلِّ
شَيۡءٖ وَهُوَ ٱلۡوَٰحِدُ ٱلۡقَهَّٰرُ ١٦

**16.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሰማያትና የምድር ጌታ ማን ነው? በላቸው፡፡ አላህ ነው በል ለነፍሶቻቸው ጥቅምንም ጉዳትን የማይችሉን ረዳቶች ከእርሱ ሌላ ያዛችሁን? በላቸው እውርና የሚያይ ይስተካከላሉን? ወይስ ጨለማዎችና ብርሃን ይስተካከላሉን? ወይስ ለአላህ እንደ እርሱ አፈጣጠር የፈጠሩን ተጋሪዎች አረጉለትና ፍጥረቱ በእነርሱ ላይ ተመሳሰለባቸውን? በል፡፡ አላህ ሁለመናውን ፈጣሪ ነው፡፡ እርሱም ብቸኛና አሸናፊ ነው በል፡፡

أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَسَالَتۡ أَوۡدِيَةُۢ بِقَدَرِهَا فَٱحۡتَمَلَ ٱلسَّيۡلُ زَبَدٗا رَّابِيٗاۖ وَمِمَّا يُوقِدُونَ عَلَيۡهِ
فِي ٱلنَّارِ ٱبۡتِغَآءَ حِلۡيَةٍ أَوۡ مَتَٰعٖ زَبَدٞ مِّثۡلُهُۥۚ كَذَٰلِكَ يَضۡرِبُ ٱللَّهُ ٱلۡحَقَّ وَٱلۡبَٰطِلَۚ فَأَمَّا ٱلزَّبَدُ
فَيَذۡهَبُ جُفَآءٗۖ وَأَمَّا مَا يَنفَعُ ٱلنَّاسَ فَيَمۡكُثُ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ كَذَٰلِكَ يَضۡرِبُ ٱللَّهُ ٱلۡأَمۡثَالَ ﴿١٧﴾

**17.** ከሰማይ ውሃን አወረደ፡፡ ሸለቆዎቹም በመጠናቸው ፈሰሱ፡፡ ጎርፉም አስፋፊውን የውሃ አረፋ ተሸከመ፡፡ ለጌጥ ወይም ለዕቃ ፍላጎት በእርሱ ላይ እሳት የሚያነዱበትም ማዕድን ብጤው የኾነ ኮረፋት አለው፡፡ እንደዚሁ አላህ ለእውነትና ለውሸት ምሳሌን ያደርጋል፡፡ የውሃ አረፋውም ግብስብስ ኾኖ ይጠፋል፡፡ ለሰዎች የሚጠቅመውማ በምድር ላይ ይቆያል፡፡ እንደዚሁ አላህ ምሳሌዎችን ይገልጻል፡፡

لِلَّذِينَ ٱسۡتَجَابُواْ لِرَبِّهِمُ ٱلۡحُسۡنَىٰۚ وَٱلَّذِينَ لَمۡ يَسۡتَجِيبُواْ لَهُۥ لَوۡ أَنَّ لَهُم مَّا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا
وَمِثۡلَهُۥ مَعَهُۥ لَٱفۡتَدَوۡاْ بِهِۦٓۚ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ سُوٓءُ ٱلۡحِسَابِ وَمَأۡوَىٰهُمۡ جَهَنَّمُۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمِهَادُ ﴿١٨﴾

**18.** ለእነዚያ ለጌታቸው ለታዘዙት ሰዎች መልካም ነገር ገነት አለላቸው፡፡ እነዚያም ለእርሱ ያልታዘዙት ለእነርሱ በምድር ያለው ሁሉ ከእርሱም ጋር ብጤው ቢኖራቸው ኖሮ በእርሱ በተበዡበት ነበር፡፡ እነዚያ ለእነርሱ ከፉ ምርመራ አለባቸው፡፡ መኖሪያቸውም ገሀነም ናት፡፡ ፍራሻቸውም (ገሀነም) ከፋች፣

۞أَفَمَن يَعۡلَمُ أَنَّمَآ أُنزِلَ إِلَيۡكَ مِن رَّبِّكَ ٱلۡحَقُّ كَمَنۡ هُوَ أَعۡمَىٰٓۚ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُوْلُواْ
ٱلۡأَلۡبَٰبِ ﴿١٩﴾ ٱلَّذِينَ يُوفُونَ بِعَهۡدِ ٱللَّهِ وَلَا يَنقُضُونَ ٱلۡمِيثَٰقَ ﴿٢٠﴾ وَٱلَّذِينَ يَصِلُونَ مَآ أَمَرَ
ٱللَّهُ بِهِۦٓ أَن يُوصَلَ وَيَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ وَيَخَافُونَ سُوٓءَ ٱلۡحِسَابِ ﴿٢١﴾ وَٱلَّذِينَ صَبَرُواْ ٱبۡتِغَآءَ
وَجۡهِ رَبِّهِمۡ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنفَقُواْ مِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ سِرّٗا وَعَلَانِيَةٗ وَيَدۡرَءُونَ بِٱلۡحَسَنَةِ
ٱلسَّيِّئَةَ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عُقۡبَى ٱلدَّارِ ﴿٢٢﴾ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ يَدۡخُلُونَهَا وَمَن صَلَحَ مِنۡ ءَابَآئِهِمۡ

وَأَزۡوَٰجِهِمۡ وَذُرِّيَّٰتِهِمۡۖ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يَدۡخُلُونَ عَلَيۡهِم مِّن كُلِّ بَابٖ ٢٣ سَلَٰمٌ عَلَيۡكُم بِمَا
صَبَرۡتُمۡۚ فَنِعۡمَ عُقۡبَى ٱلدَّارِ ٢٤

**19-24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደው ሁሉ እውነት መኾኑን የሚያውቅ ሰው ልክ እንደዚያ እርሱ እውር እንደ ኾነው ሰው ነውን? የሚገሠፁት የአእምሮ ባለቤቶች ብቻ ናቸው። እነዚያ የአላህን ቃል ኪዳን የሚሞሉ የጠበቀውንም ኪዳን የማያፈርሱ ናቸው። እነዚያም አላህ እንዲቀጠል በእርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቀጥሉ ጌታቸውንም የሚያከብሩ መጥፎንም ቁጥጥር የሚፈሩ ናቸው። እነዚያም የጌታቸውን ውዴታ ለመፈለግ የታገሱ ሶላትንም አዘውትረው የሰገዱ ሰዎች እኛ ከሰጠናቸው ሲሳይም በምስጢርም ኾነ በግልጽ የመፀወቱ ክፉውንም በበጎ የሚገፈትሩ ናቸው። እነዚያ ለእነርሱ መጨረሻይቱ ምስጉን አገር አለችላቸው። እርሷም የመኖሪያ ገነቶች ናት። ይገቡባታል። ከአባቶቻቸውም ከሚስቶቻቸውም ከዝርያቸውም መልካም የሠራ ሰው ሁሉ ይገባበታል። መላዕክትም በእነርሱ ላይ ከየደጃፉ ሁሉ ይገባሉ። ሰላም ለእናንተ ይኹን። ይህ ምንዳ በመታገሳችሁ የተሰጣችሁ ነው። የመጨረሻይቱም አገር ምን ታምር፣ ይሏቸዋል።

وَٱلَّذِينَ يَنقُضُونَ عَهۡدَ ٱللَّهِ مِنۢ بَعۡدِ مِيثَٰقِهِۦ وَيَقۡطَعُونَ مَآ أَمَرَ ٱللَّهُ بِهِۦٓ أَن يُوصَلَ
وَيُفۡسِدُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱللَّعۡنَةُ وَلَهُمۡ سُوٓءُ ٱلدَّارِ ٢٥

**25.** እነዚያ የአላህን ቃል ኪዳን ከጠበቀ በኋላ የሚያፈርሱ አላህ እንዲቀጠል በእርሱ ያዘዘውን ነገር የሚቆርጡ፣ በምድርም ላይ የሚያበላሹ እነዚያ ለእነርሱ እርግማን አለባቸው። ለእነርሱም መጥፎ አገር ገሀነም አለላቸው።

ٱللَّهُ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقۡدِرُۚ وَفَرِحُواْ بِٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا
وَمَا ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَا فِي ٱلۡأٓخِرَةِ إِلَّا مَتَٰعٞ ٢٦

**26.** አላህ ለሚሻው ሰው ሲሳይን ያሰፋል ያጠባልም ከሃዲዎች በቅርቢቱም ሕይወት ተደሰቱ የቅርቢቱም ሕይወት በመጨረሻይቱ አንጻር ትንሽ መጠቀሚያ እንጂ ምንም አይደለችም።

وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَوۡلَآ أُنزِلَ عَلَيۡهِ ءَايَةٞ مِّن رَّبِّهِۦۗ
قُلۡ إِنَّ ٱللَّهَ يُضِلُّ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِيٓ إِلَيۡهِ مَنۡ أَنَابَ ٢٧

**27.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች በእርሱ ላይ ከጌታው ተአምር ለምን አልተወረደም ይላሉ። አላህ የሚሻውን ሰው ያጠምማል። የተመለሰውንም ሰው ወደ እርሱ ይመራል በላቸው።

ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَتَطۡمَئِنُّ قُلُوبُهُم بِذِكۡرِ ٱللَّهِۗ أَلَا بِذِكۡرِ ٱللَّهِ تَطۡمَئِنُّ ٱلۡقُلُوبُ ﴿٢٨﴾ ٱلَّذِينَ
ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ طُوبَىٰ لَهُمۡ وَحُسۡنُ مَـَٔابٖ ﴿٢٩﴾

**28-29.** እነርሱም እነዚያ በአላህ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው። ንቁ፣ አላህን በማውሳት ልቦች ይረካሉ። እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ስራዎችን የሠሩት ለእነርሱ ደግ ኑሮና መልካም መመለሻ አለላቸው።*

* (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህን በሚያስታውሰውና አላህን በማያስታውስ ሰው መካከል ያለው ምሳሌ ልክ በሕይወት እንዳለና እንደ ሞተ ነው።»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «በቀን ውስጥ አንድ መቶ ጊዜ «ሱብሃነኋሁ ወቢ ሐምዲሂ»ያለ ወንጀሎቹ ባህር ላይ እንደሚታይ አረፋ ቢሆኑም እንኳ በሙሉ ይማርለታል» ቡኻሪ ዘግበውታል።

(ሐ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «በቀን ውስጥ አንድ መቶ ጊዜ «ላ ኢላሀ ኢልለሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪከ ለሁ ለሁል ሙልክ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩሊ ሸይኢን ቀዲር» ያለ ሰው አስር ባሪያዎችን ነፃ እንዳወጣ ተደርጎ ምንዳ ይፃፍለታል። አንድ መቶ የመልካም ስራዎች ምንዳም በስራው መዝገብ ውስጥ ይመዘግብለታል። ይህ አባባሉ የዚያን ቀን ሙሉ ከሰይጣን መከላከያ ይሆነዋል። ይህ ሰው ካደረገው በበለጠ ሁኔታ ከሚሰራው ሰው በስተቀር ማንም ሰው እንደዚህ መልካም ነገር አይሰራም።»

كَذَٰلِكَ أَرۡسَلۡنَٰكَ فِيٓ أُمَّةٖ قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهَآ أُمَمٞ لِّتَتۡلُوَاْ عَلَيۡهِمُ ٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَهُمۡ
يَكۡفُرُونَ بِٱلرَّحۡمَٰنِۚ قُلۡ هُوَ رَبِّي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ عَلَيۡهِ تَوَكَّلۡتُ وَإِلَيۡهِ مَتَابِ ﴿٣٠﴾

**30.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልክ እንደዚሁ ከበፊትዋ ብዙ ሕዝቦች በእርግጥ ያለፉ ወደ ኾነችው ሕዝብ እነርሱ በአልረህማን የሚክዱ ሲኾኑ ያንን ወደ አንተ ያወረድነውን ቁርኣን በእነርሱ ላይ ታነብላቸው ዘንድ ላክንህ። እርሱ አልረህማን ጌታዬ ነው። ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ አምላክ የለም። በእርሱ ላይ ብቻ ተመካሁ መመለሻዬም ወደ እርሱ ብቻ ነው በላቸው።

وَلَوۡ أَنَّ قُرۡءَانٗا سُيِّرَتۡ بِهِ ٱلۡجِبَالُ أَوۡ قُطِّعَتۡ بِهِ ٱلۡأَرۡضُ أَوۡ كُلِّمَ بِهِ ٱلۡمَوۡتَىٰۗ بَل لِّلَّهِ ٱلۡأَمۡرُ
جَمِيعًاۗ أَفَلَمۡ يَاْيۡـَٔسِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَن لَّوۡ يَشَآءُ ٱللَّهُ لَهَدَى ٱلنَّاسَ جَمِيعٗاۗ وَلَا يَزَالُ ٱلَّذِينَ
كَفَرُواْ تُصِيبُهُم بِمَا صَنَعُواْ قَارِعَةٌ أَوۡ تَحُلُّ قَرِيبٗا مِّن دَارِهِمۡ حَتَّىٰ يَأۡتِيَ وَعۡدُ ٱللَّهِۚ
إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُخۡلِفُ ٱلۡمِيعَادَ ﴿٣١﴾

31. ቁርአን በእርሱ ተራራዎች በተነዱበት ወይም በእርሱ ምድር በተቆራረጠችበት ወይም በእርሱ ሙታን እንዲናገሩ በተደረጉበት ኖሮ የመካ ከሓዲያን ባላመኑ ነበር በእውነቱ ነገሩ ሁሉ የአላህ ነው። እነዚያ ያመኑት ሰዎች እነሆ አላህ በሻ ኖሮ ሰዎችን በመላ በእርግጥ ወደ ቀናው መንገድ ይመራቸው እንደ ነበረ አያውቁምን? እነዚያን የካዱት በሥራቸው ምክንያት አጥፊ አደጋ የምታገኛቸው ከመኾን ወይም የአላህ ቀጠሮ እስኪ መጣ በአገራቸው አቅራቢያ አንተ የምትሰፍርባቸው ከመኾን አይወገዱም። አላህ ቀጠሮውን አያፈርስምና።

وَلَقَدِ ٱسْتُهْزِئَ بِرُسُلٍ مِّن قَبْلِكَ فَأَمْلَيْتُ لِلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ثُمَّ أَخَذْتُهُمْ ۖ فَكَيْفَ كَانَ عِقَابِ ﴿٣٢﴾

32. ከአንተ በፊት የነበሩትም መልዕክተኞች በእርግጥ ተላግጦባቸው ነበር። እናም ለእነዚያ ለካዱት ጊዜን ሰጠኋቸው። ከዚያ (በቅጣት) ያዝኳቸው። ቅጣቴ እንዴት ነበር! (ምን ያህል የከፋ ነበር)።

أَفَمَنْ هُوَ قَآئِمٌ عَلَىٰ كُلِّ نَفْسٍۭ بِمَا كَسَبَتْ ۗ وَجَعَلُوا۟ لِلَّهِ شُرَكَآءَ قُلْ سَمُّوهُمْ ۚ أَمْ تُنَبِّـُٔونَهُۥ بِمَا لَا يَعْلَمُ فِى ٱلْأَرْضِ أَم بِظَٰهِرٍ مِّنَ ٱلْقَوْلِ ۗ بَلْ زُيِّنَ لِلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مَكْرُهُمْ وَصُدُّوا۟ عَنِ ٱلسَّبِيلِ ۗ وَمَن يُضْلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِنْ هَادٍ ﴿٣٣﴾ لَّهُمْ عَذَابٌ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَلَعَذَابُ ٱلْءَاخِرَةِ أَشَقُّ ۖ وَمَا لَهُم مِّنَ ٱللَّهِ مِن وَاقٍ ﴿٣٤﴾

33-34. (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱ በነፍስ ሁሉ ላይ በሰራችው ሥራ ተጠባባቂ (የኾነው) አላህ እንደዚህ እንዳልኾነው ጣዖት ብጤ ነውን? ለአላህ ተጋሪዎችን አደረጉ። ጥሯቸው። አላህን በምድር ውስጥ የማያውቀው ነገር ኖሮ ትነግሩታላችሁን? ወይስ ከቃል በግልጽ ፍቺ በሌለው ከንቱ ቃል ተጋሪዎቹ በማለት (ትጠሯቸዋላችሁን?) በላቸው። በእውነቱ ለእነዚያ ለካዱት ተንኮላቸው ተሸለመላቸው። ከእውነቱ መንገድም ታገዱ። አላህ ያጠመመውን ሰው ምንም አቅኚ የለውም። ለእነርሱ በቅርቢቱ ሕይወት ቅጣት አለባቸው። የመጨረሻይቱም ዓለም ቅጣት በጣም የበረታ ነው። ለእነርሱ ከአላህ (ቅጣት) ምንም ጠባቂ የላቸውም።

۞ مَّثَلُ ٱلْجَنَّةِ ٱلَّتِى وُعِدَ ٱلْمُتَّقُونَ ۖ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ ۖ أُكُلُهَا دَآئِمٌ وَظِلُّهَا ۚ تِلْكَ عُقْبَى ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوا۟ ۖ وَّعُقْبَى ٱلْكَٰفِرِينَ ٱلنَّارُ ﴿٣٥﴾

35. ያች ጥንቁቆች ተስፋ የተሰጧት ገነት ምጣኔዋ (ምሳሌዋ) (እንደሚነገራችሁ ነው) ከሥርዋ ወንዞች ይፈሳሉ። ምግቧ ሁል ጊዜ የማያቋረጥ ነው። ጥላዋም (እንደዚሁ) ይህች ገነት የእነዚያ የተጠነቀቁት መጨረሻ ናት። የከሓዲያን መጨረሻ ግን እሳት ናት።

وَٱلَّذِينَ ءَاتَيْنَٰهُمُ ٱلْكِتَٰبَ يَفْرَحُونَ بِمَآ أُنزِلَ إِلَيْكَ ۖ وَمِنَ ٱلْأَحْزَابِ مَن يُنكِرُ بَعْضَهُۥ ۚ
قُلْ إِنَّمَآ أُمِرْتُ أَنْ أَعْبُدَ ٱللَّهَ وَلَآ أُشْرِكَ بِهِۦٓ ۚ إِلَيْهِ أَدْعُوا۟ وَإِلَيْهِ مَـَٔابِ ﴿٣٦﴾

36. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ መጽሐፉን የሰጠናቸውን ወደ አንተ በተወረደው ይደሰታሉ። ከአህዛብም ከፊሉን የሚክዱ ሰዎች አሉ። እኔ የታዘዝኩት አላህን ብቻ እንድገዛና በእርሱም እንዳላጋራ ነው። ወደ እርሱ እጠራለሁ። መመለሻዬም ወደ እርሱ ነው በላቸው።

وَكَذَٰلِكَ أَنزَلْنَٰهُ حُكْمًا عَرَبِيًّا ۚ وَلَئِنِ ٱتَّبَعْتَ أَهْوَآءَهُم بَعْدَ مَا جَآءَكَ مِنَ ٱلْعِلْمِ
مَا لَكَ مِنَ ٱللَّهِ مِن وَلِىٍّ وَلَا وَاقٍ ﴿٣٧﴾

37. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልክ እንደዚሁ በአረብኛ የተነገረ ፍትህ ሲኾን አወረድነው። እውቀቱ ከመጣልህም በኋላ ዝንባሌዎቻቸውን ብትከተል ከአላህ ቅጣት ወዳጅም ሆነ ጠባቂ ምንም የለህም።

وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلًا مِّن قَبْلِكَ وَجَعَلْنَا لَهُمْ أَزْوَٰجًا وَذُرِّيَّةً ۚ وَمَا كَانَ لِرَسُولٍ أَن يَأْتِىَ بِـَٔايَةٍ
إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۗ لِكُلِّ أَجَلٍ كِتَابٌ ﴿٣٨﴾

38. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት ብዙ መልዕክተኞችን በእርግጥ ልከናል። ለእነርሱም ሚስቶችንና ልጆችን አድርገናል። ለማንኛውም መልዕክተኛ በአላህ ፈቃድ እንጂ ተአምር ሊያመጣ አይገባውም። ለጊዜው ሁሉ ጽሑፍ አለው።

يَمْحُوا۟ ٱللَّهُ مَا يَشَآءُ وَيُثْبِتُ ۖ وَعِندَهُۥٓ أُمُّ ٱلْكِتَٰبِ ﴿٣٩﴾

39. አላህ የሚፈልገውን ያብሳል። የሚሻውን ያፀድቃል። የመጽሐፉ ዋና መሠረትም እርሱ ዘንድ ብቻ ነው።

وَإِن مَّا نُرِيَنَّكَ بَعۡضَ ٱلَّذِى نَعِدُهُمۡ أَوۡ نَتَوَفَّيَنَّكَ فَإِنَّمَا عَلَيۡكَ ٱلۡبَلَٰغُ وَعَلَيۡنَا ٱلۡحِسَابُ ﴿٤٠﴾

**40.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዚያን ያስፈራራናቸውን ቅጣት ከፊሉን በሕይወት እያለህ ብናሳይህ መልካም ነው። ወይም ሳናሳይህ ብንገድልህ ወቀሳ የለብህም። በአንተ ላይ ያለብህ ማድረስ ብቻ ነው። ምርመራው ግን በእኛ ላይ ነው።

أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّا نَأۡتِى ٱلۡأَرۡضَ نَنقُصُهَا مِنۡ أَطۡرَافِهَاۚ وَٱللَّهُ يَحۡكُمُ لَا مُعَقِّبَ لِحُكۡمِهِۦۚ وَهُوَ سَرِيعُ ٱلۡحِسَابِ ﴿٤١﴾

**41.** እኛ ምድርን ከጫፎችዋ የምናጎድላት ኾነን የምናመጣባት መኾናችንን አላወቁምን (አላዩምን)?። አላህ ይፈርዳል። ለፍርዱም ገልባጭ የለውም። እርሱም ምርመራው ፈጣን ነው።

وَقَدۡ مَكَرَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ فَلِلَّهِ ٱلۡمَكۡرُ جَمِيعًاۖ يَعۡلَمُ مَا تَكۡسِبُ كُلُّ نَفۡسٍۗ وَسَيَعۡلَمُ ٱلۡكُفَّٰرُ لِمَنۡ عُقۡبَى ٱلدَّارِ ﴿٤٢﴾

**42.** እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ሰዎች በእርግጥ መከሩ (አሴሩ)። አዘንግቶም የመያዙ ዘዴ በሙሉ የአላህ ብቻ ነው። አላህ ነፍስ ሁሉ የምትሰራውን ያውቃል። ከሓዲያን የመጨረሻይቱ አገር ለማን እንደምትኾን ወደፊት ያውቃሉ።

وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَسۡتَ مُرۡسَلٗاۚ قُلۡ كَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدَۢا بَيۡنِى وَبَيۡنَكُمۡ وَمَنۡ عِندَهُۥ عِلۡمُ ٱلۡكِتَٰبِ ﴿٤٣﴾

**43.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች መልእክተኛ አይደለህም ይላሉ። በእኔና በእናንተ መካከል መስካሪ በአላህና እርሱ ዘንድ የመጽሐፉ እውቀት ባለው ሰው በቃ በላቸው።

**ከነጎድጓድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-43) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ከአላህ የሚመጡ መልዕክቶችን አሚን ብሎ መቀበልና የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማመን ተገቢ መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. በአንድ አምላክ ማመን አስፈላጊ መሆኑንና እሱም አላህ መሆኑን ማረጋገጥ
3. ሙቶ መነሳት ሐቅ መሆኑንና ሰው በዚህች አለም በሰራው የሚጠየቅ መሆኑን ማረጋገጥ፤
4. በዚህች ዓለም ፍጡር መመራመር ያለው ደረጃ ከፍተኛ መሆኑን መግለፅ፤
5. አዕምሮ እውነትን ተመራምሮ ለማግኘት ያለው ጥቅም ምን እንደሆነ፤
6. የእምነት መሰረቶች ተውሒድ፤ ነብያትን ማመን ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤

7. የእምነት ፀሮች የሆኑት በጭፍን መከተል፣ ኩራት፣ ትዕቢት መሆናቸውን፣
8. የአላህ ትልቅነትና የእውቀቱን ስፋት፣
9. እኛ ሰዎች በቀደና በቀደር ማመን ትርጉሙን ማወቅ እንዳለብን፣
10. የእውነት አምላክ የእውነት አስተምህሮት የአላህ ብቻ መሆኑን፣
11. የካፊሮች ዱዓ ተቀባይነት እንደሌለው፣
12. ፍጡር ሁሉ በውድም ሆነ በግድ የአላህ ታዛዥ እንደሆነ፣
13. የሺርክን መጥፎነትና የአዕምሯዊም ሆነ የሰማያዊ ማስረጃ የሌለው መሆኑን፣
14. አስተምህሮትን ለማቅረብ ምሳሌዎችን መጥቀስ ተፈላጊ መሆኑን፣
15. ትክክለኛ እምነት ያለውን ፅናትና የውሸትን ደካማነት፣
16. ለእነዚያ ለጌታቸው ለታዘዙት መልካም ነገር ቃል የተገባላቸው መሆኑን፣
17. ትክክለኛ አማኝ ህያው የሚያይ የሚያውቅና የሚተገብር ሲሆን በአንፃሩ ከሃዲ ግን ሙት ማየትና ማስተዋል የማይችል እና ተግባር የሌለው መሆኑን።
18. በምክሮች መገሰፅ ለትክክለኛ አዕምሮ ባለቤት መሆኑን፣
19. በእነዚህ ስምንት አናቅፅ የተወሱት ባህሪያት አስፈላጊነቱን፣
20. መላኢኮች የጀነት ሰዎችን ወደጀነት ሲገቡ እንደሚያበስሯቸው፣
21. የእደለ ቢሶችን ባህሪ ከመላበስ መጠንቀቅ እንደሚገባ፣
22. ሀብትም ሆነ ድህነት የአላህን ውዴታ ለማመልከት ሳይሆን ለፈተና የሚደረግ መሆኑን፣
23. የዱንያን ምንነት መረዳትና የዚህችን ዓለም ድክመት መረዳት፣
24. አላህን ማውሳት ካለው ጥቅም አንዱ የልብ መረጋጋት መሆኑን፣
25. ለትክክለኛ አማኞች ጡባ የተባለ ጀነት እንደተዘጋጀላቸው፣
26. የተውሒድን ትልቅነት ማስተማር፣
27. መመካት በአንድ አላህ ብቻ እንደሆነ ንሰሃ መግባትም ወደ እሱው ብቻ መሆኑን፣
28. የቁርኣንን ትልቅነትና ክብሩን፣
29. አላህ ከሓዲያንን እስከ ዐለም ፍፃሜ ድረስ መቅሰፍት ሊያመጣባቸው እንደሚችል መዛቱን፣
30. አላህ ጊዜ በሚሰጥና ቢያዘገይ ለአንደኛው የማይተው መሆኑን፣
31. ጣኦት ለራሱ እንኳን የማይበቃ እራሱን መጠበቅ የማይችል መሆኑን መግለፅ፣
32. ከሓዲያንን ከክህደት እንዳይመለሱ የሚያደርገው ሰይጣን መሆኑን፣
33. ማብሰርና ማስደንገጥ ምርጥ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን፣
34. የትኛውም ውሳኔ መነሻው ቁርኣን ከዚያም ሐዲስ ከዚያም ንፅፅርና ከዚያም የምሁራን ስምምነት መሆኑን፣
35. የስሜትና የቢድዓ ባለቤቶችን በጭፍን ከመከተል ማስጠንቀቅ፣
36. የቀደና የቀድርን ጉዳይ በትኩረት ማስተማር፣
37. በቁርኣን በሐዲስ ውስጥ መሻር ያለ መሆኑን፣
38. ኢስላም በሩብ ምዕተ አመት ብቻ ያን ያህል መስፋፋቱ እውነት ለመሆኑ ማስረጃ መሆኑን፣
39. የአላህ ህግጋት በማንም እንደማይታጠፍና በይግባኝ መሻር እንደማይቻል፣
40. የአላህ ምስክርነት ከምስክሮች ሁሉ የበለጠና ከእሱ ምስክር በኋላ የማንም ምስክር እንደማያስፈልግ፣
41. አዋቂዎች ከመሀይሞች እንደሚበልጡ በግልፅ እንገራለን።

በአላህ ፈቃድ የነጎድጓድ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (14)
# የነብዩ ኢብራሂም ምዕራፍ
## (ሱረቱ ኢብራሂም)

سُورَةُ إِبْرَاهِيمَ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (52) ናቸው።
### የሱረቱ ኢብራሂም መግቢያ

ይህን ስያሜ ያገኘው በዚሁ ምዕራፍ በ (35) ኛው አንቀፅ ላይ ታሪካቸው በተወሱት ነብይ ስም ነው የተሰየመው። ይህ ነብይ በቁርኣን ውስጥ በሀያ ዘጠኝ ምራፍ (69) ጊዜ ታሪካቸው ተወስቷል። እንደሌሎቹ በመካ የወረዱ ምእራፎች ትኩረቱን በአቂዳ ላይ ያደርጋል። በተለይ ስለ ነብዩ (ﷺ) ጠቅላላ ነብይነት በሰፊው ዘግቧል። ስለ ነብዩ ሙሳ አስተምህሮትና የሕዝቦች መልስ እንዲሁም የኢብራሒምን ታሪክ በሰፊው ይዘረዝራል። ስለ ነብይነት የሰጠውን ትኩረት በማጠናከር ያብራራል። ወደዚህ ዓለም ፍጥረታት ትኩረት ሰጥተን እንድንመራመር ግፊት አሳድሮ ሰዎች ቁርኦንን ከመቀበል አንጻር ያላቸውን ልዩ ልዩ ሁኔታዎች በመጥቀስ ያስተምራል። የሙዕሚኖችን ባህሪ አንስቶ የከሓዲያንንም ግልጽ ትዕቢት ዘርዝሯል።

በማስከተልም አላህ ነብዩ (ﷺ) ይጽናኑ ዘንድ የከሓዲያን ፌዝ ለእሳቸው ብቻ እንዳልነበረና ከእሳቸውም በፊት የነበሩት ነብያት የዚሁ ተመሳሳይ ስቃይ እንደደረሰባቸው ማስታወሱን ለሁሉም ተገቢው ምንዳ እንደሚሰጥ፤ ቁርኣንም እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ታላቅ ተዓምር እንደሚሆን፤ አላህ ነብያትን የሚረዳበት ተዓምር እርሱ በፈለገው እንጂ ሰዎች በጠየቁት መሠረት እንደማይሆን በግልጽ ማስረዳቱን አብራርቶ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓرۚ كِتَٰبٌ أَنزَلۡنَٰهُ إِلَيۡكَ لِتُخۡرِجَ ٱلنَّاسَ مِنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ بِإِذۡنِ رَبِّهِمۡ إِلَىٰ صِرَٰطِ
ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَمِيدِ ١

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ራ፤* (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ይህ ቁርአን) ሰዎችን በጌታቸው ፈቃድ ከጨለማ ወደ ብርሃን አሸናፊ፣ ምስጉን ወደ ሆነው ጌታ መንገድ ታወጣ ዘንድ ወደ አንተ ያወረድነው መጽሐፍ ነው።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርአን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

ٱللَّهِ ٱلَّذِي لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۗ وَوَيۡلٞ لِّلۡكَٰفِرِينَ مِنۡ عَذَابٖ شَدِيدٍ ٢
ٱلَّذِينَ يَسۡتَحِبُّونَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا عَلَى ٱلۡأٓخِرَةِ وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَيَبۡغُونَهَا عِوَجًاۚ
أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلِۭ بَعِيدٖ ٣

**2-3.** አላህ ያ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ የሆነ ነው። ለከሓዲያንም ከብርቱ ቅጣት ወዮላቸው። እነዚያ የቅርቢቱን ህይወት ከመጨረሻይቱ ህይወት ይበልጥ የሚወዱና ከአላህ መንገድ ሰዎችን የሚያግዱ መጥመሟንም የሚፈልጓት ናቸው። እነዚያ በሩቅ ስህተት ውስጥ ናቸው።

وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن رَّسُولٍ إِلَّا بِلِسَانِ قَوۡمِهِۦ لِيُبَيِّنَ لَهُمۡۖ فَيُضِلُّ ٱللَّهُ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِي مَن
يَشَآءُۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٤

**4.** ከመልዕክተኞች ማንኛውንም ለእነርሱ ያብራራላቸው ዘንድ በወገኖቹ ቋንቋ እንጂ በሌላ አልላክንም። አላህም የሚፈልገውን ያጠምማል የሚፈልገውን ያቀናል። እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَآ أَنۡ أَخۡرِجۡ قَوۡمَكَ مِنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ وَذَكِّرۡهُم بِأَيَّىٰمِ
ٱللَّهِۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّكُلِّ صَبَّارٖ شَكُورٖ ٥ وَإِذۡ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوۡمِهِ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَةَ ٱللَّهِ
عَلَيۡكُمۡ إِذۡ أَنجَىٰكُم مِّنۡ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ يَسُومُونَكُمۡ سُوٓءَ ٱلۡعَذَابِ وَيُذَبِّحُونَ أَبۡنَآءَكُمۡ

وَيَسۡتَحۡيُونَ نِسَآءَكُمۡۚ وَفِي ذَٰلِكُم بَلَآءٞ مِّن رَّبِّكُمۡ عَظِيمٞ ٦ وَإِذۡ تَأَذَّنَ رَبُّكُمۡ لَئِن
شَكَرۡتُمۡ لَأَزِيدَنَّكُمۡۖ وَلَئِن كَفَرۡتُمۡ إِنَّ عَذَابِي لَشَدِيدٞ ٧ وَقَالَ مُوسَىٰٓ إِن تَكۡفُرُوٓاْ أَنتُمۡ
وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا فَإِنَّ ٱللَّهَ لَغَنِيٌّ حَمِيدٌ ٨

**5-8.** ሙሳን ወገኖችህን ከጨለማዎች ወደ ብርሃን አውጣ። የአላህን ቀኖች አስገንዝባቸው በማለት በተአምራታችን (አጠናክረን) በእርግጥ ላክነው። በዚህ ውስጥ በብዙ ታጋሽና በብዙ አመስጋኝ ለሆኑት ሁሉ በእርግጥ ተአምራቶች አሉበት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳ ለህዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ) ከፈርኦን ቤተሰቦች መጥፎን ቅጣት የሚያቀምሷችሁ፣ ወንዶች ልጆቻችሁን የሚያርዱና ሴቶቻችሁን የሚተው ሲሆን በአዳናችሁ ጊዜ በእናንተ ላይ የዋለላችሁን የአላህን ፀጋ አስታውሱ። በዚሃችሁ ከጌታችሁ የሆነ ታላቅ ፈተና አለበት። ጌታችሁም ባለ ጊዜ የሆነውን አስታውስ ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ። ብትክዱም እቀጣችኋለሁ። ቅጣቴ በእርግጥ ብርቱ ነውና በማለት ባስታወቀ ጊዜ (አስታውሱ)። ሙሳ፡- እናንተም በምድር ያለውም ሁሉ በመላ ብትክዱ አላህ ተብቃቂ ምስጉን ነው አለ።

**ከኢብራሂም ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *ቁርኣንን ለሚያስተባብሉ ሰዎች ስህተታቸውን ማስረዳት፤*
2. *ክህደት በጨለማ፤ እምነት ደግሞ በብርሃን እንደሚመሰል፤*
3. *አላህ ነብያትን በየህዝቦቻቸው ቋንቋ ያስተምሩ ዘንድ መላኩን፤*
4. *ሂዳያ መስጠት የሚችለው አላህ ብቻ መሆኑንና ወደቀናው መንገድ የመምራት ብቸኛ ባለሙብት እርሱ መሆኑን፤*
5. *ትዕግስትና አላህን ማመስገን በአላህ ዘንድ ያላቸው ምንዳ ተደራራቢ መሆኑን እንማራለን።*

أَلَمۡ يَأۡتِكُمۡ نَبَؤُاْ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكُمۡ قَوۡمِ نُوحٖ وَعَادٖ وَثَمُودَ وَٱلَّذِينَ مِنۢ بَعۡدِهِمۡ لَا يَعۡلَمُهُمۡ
إِلَّا ٱللَّهُۚ جَآءَتۡهُمۡ رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَرَدُّوٓاْ أَيۡدِيَهُمۡ فِيٓ أَفۡوَٰهِهِمۡ وَقَالُوٓاْ إِنَّا كَفَرۡنَا بِمَآ
أُرۡسِلۡتُم بِهِۦ وَإِنَّا لَفِي شَكّٖ مِّمَّا تَدۡعُونَنَآ إِلَيۡهِ مُرِيبٖ ٩

**9.** (ሙስሊሞች ሆይ!) የእነዚያ ከናንተ በፊት የነበሩት የኑህ ህዝቦች፣ የዓድም የሠሙድም የእነዚያም ከእነርሱ በኋላ የነበሩት ከአላህ በስተቀር ሌላ የማያውቃቸው ህዝቦች ወሬ (ታሪክ) አልመጣላችሁምን? መልዕክተኞቻቸው በማስረጃዎች መጡላቸውና እጆቻቸውን በቁጭት ሊነክሱ ወደ አፎቻቸው መለሱ፡- በተላካችሁበት ነገር ካድን እኛም ወደ እርሱ ከምትጠሩን ነገር አወላዋይ በሆነ ጥርጣሬ ውስጥ ነን አሉ።

﴿قَالَتْ رُسُلُهُمْ أَفِي ٱللَّهِ شَكٌّ فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ يَدْعُوكُمْ لِيَغْفِرَ لَكُم مِّن
ذُنُوبِكُمْ وَيُؤَخِّرَكُمْ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۚ قَالُوٓا۟ إِنْ أَنتُمْ إِلَّا بَشَرٌ مِّثْلُنَا تُرِيدُونَ أَن تَصُدُّونَا
عَمَّا كَانَ يَعْبُدُ ءَابَآؤُنَا فَأْتُونَا بِسُلْطَٰنٍ مُّبِينٍ ﴿١٠﴾ قَالَتْ لَهُمْ رُسُلُهُمْ إِن نَّحْنُ إِلَّا بَشَرٌ
مِّثْلُكُمْ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَمُنُّ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ ۖ وَمَا كَانَ لَنَآ أَن نَّأْتِيَكُم بِسُلْطَٰنٍ
إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ﴿١١﴾ وَمَا لَنَآ أَلَّا نَتَوَكَّلَ عَلَى ٱللَّهِ وَقَدْ هَدَىٰنَا
سُبُلَنَا ۚ وَلَنَصْبِرَنَّ عَلَىٰ مَآ ءَاذَيْتُمُونَا ۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُتَوَكِّلُونَ ﴿١٢﴾

**10-12.** መልዕክተኞቻቸው ከኃጢአቶቻችሁ እንዲያስምሯችሁ ወደ ተወሰነ ጊዜም ያለ ቅጣት እንዲያቆያችሁ የሚጠራችሁ ሲሆን ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ በሆነው አላህ በመኖሩ ጥርጣሬ አለን? አሏቸው። ህዝቦቹም፡ እናንተ ብጤያችን ሰው እንጂ (ሌላ ፍጡር) አይደላችሁም። አባቶቻችን ይገዙት ከነበሩት ልትከለክሉን ትሻላችሁን? ግልጽን አስረጅ ካመጣችሁት ሌላ አምጡልን አሉ። መልዕክተኞቻቸው እኛ ብጤያችሁ ሰዎች እንጂ ሌላ አይደለንም። ግን አላህ ከባሮቹ መካከል በሚሻው ሰው ላይ ይለግሳል። እኛም በአላህ ፈቃድ እንጂ ማስረጃን ልናመጣላችሁ አይገባንም። በአላህ ላይ ብቻ ምእመናኖች ይጠጉ (ይመኩ)። መንገዳችንን የመራን ሲሆን በአላህ ላይ የማንመካበት ለኛ ምን አለን? በማሰቃየታችሁም ላይ በእርግጥ እንታገሳለን። በአላህ ላይ ብቻ ተመኪዎች ሁሉ ይመኩ።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لِرُسُلِهِمْ لَنُخْرِجَنَّكُم مِّنْ أَرْضِنَآ أَوْ لَتَعُودُنَّ فِى مِلَّتِنَا ۖ
فَأَوْحَىٰٓ إِلَيْهِمْ رَبُّهُمْ لَنُهْلِكَنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٣﴾ وَلَنُسْكِنَنَّكُمُ ٱلْأَرْضَ مِنۢ بَعْدِهِمْ ۚ
ذَٰلِكَ لِمَنْ خَافَ مَقَامِى وَخَافَ وَعِيدِ ﴿١٤﴾

**13-14.** እነዚያ በአላህ የካዱት ለመልእክተኞቻቸው ከምድራችን በእርግጥ እናስወጣችኋለን ወይም ወደ ሃይማኖታችን በእርግጥ ትመለሳላችሁ አሉ። ወደ እነርሱም ጌታቸው እንዲህ ሲል ላከ። (ከሓዲያን) በዳዮችን በእርግጥ እናጠፋለን። ከእነርሱ በኋላም በምድሪቱ እናስቀምጣችኋለን። ይህ በፊቴ መቆሙን ለሚፈራና ዛቻዬን ለሚፈራ ሰው ነው።

وَٱسۡتَفۡتَحُواْ وَخَابَ كُلُّ جَبَّارٍ عَنِيدٍ ﴿١٥﴾ مِّن وَرَآئِهِۦ جَهَنَّمُ وَيُسۡقَىٰ مِن مَّآءٍ صَدِيدٍ ﴿١٦﴾
يَتَجَرَّعُهُۥ وَلَا يَكَادُ يُسِيغُهُۥ وَيَأۡتِيهِ ٱلۡمَوۡتُ مِن كُلِّ مَكَانٍ وَمَا هُوَ بِمَيِّتٍۖ
وَمِن وَرَآئِهِۦ عَذَابٌ غَلِيظٌ ﴿١٧﴾

**15-17.** እርዳታንም ከአላህ ፈለጉ (ተረዱም) ጨካኝ ሞገደኛ የሆነም ሁሉ አፈረ። ከስተፊቱ ገሀነም አለበት። እኹ ከሆነም ውሃ ይጋታል። ይጎነጨዋል ሊውጠውም አይቀርብም።* ሞትም ከየስፍራው ሁሉ ይመጣበታል። እርሱም የሚሞት አይደለም። ከበስተፊቱም ከባድ ቅጣት አለ።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የአንድ ከሃዲ በትከሻዎች መካከል ያለው ርቀት ፈጣን ፈረስ ጋላቢ በሶስት ቀናት ከሚጨርሰው ርቀት ጋር እኩል ይሆናል።»

مَّثَلُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِرَبِّهِمۡۖ أَعۡمَٰلُهُمۡ كَرَمَادٍ ٱشۡتَدَّتۡ بِهِ ٱلرِّيحُ فِي يَوۡمٍ عَاصِفٖۖ
لَّا يَقۡدِرُونَ مِمَّا كَسَبُواْ عَلَىٰ شَيۡءٖۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلضَّلَٰلُ ٱلۡبَعِيدُ ﴿١٨﴾

**18.** የእነዚያ በጌታቸው የካዱት ሰዎች መልካም ሥራዎቻቸው ምሳሌ በነፋሻ ቀን ነፋስ በርሱ እንደ በረታችበት አመድ ነው። በሠሩት ሥራ በምንም ላይ ሊጠቀሙ አይችሉም ይህ እርሱ ሩቅ ጥፋት ነው።

أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۚ إِن يَشَأۡ يُذۡهِبۡكُمۡ وَيَأۡتِ بِخَلۡقٖ جَدِيدٖ ﴿١٩﴾
وَمَا ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ بِعَزِيزٖ ﴿٢٠﴾

**19-20.** (የሰው ልጅ ሆይ)፣ አላህ ሰማያትንና ምድርን በእውነት የፈጠረ መሆኑን አታይምን? ቢሻ ያጠፋችኋል። አዲስ ፍጡርንም ያመጣል። ይህም (እናንተን አጥፍቶ አዲስ ፍጥረትን ማምጣት) በአላህ ላይ አስቸጋሪ ጉዳይ አይደለም።

**ከኢብራሂም ምዕራፍ ከአንቀፅ (6-20) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሰዎች የአላህን ፀጋ እንዲያስታውሱ፤
2. የእርሱን ውለታዎችን ማስታወስ ያለውን ተገቢነትና የአላህን ውለታ በመረዳት ለርሱ ምስጋናን ማቅረብ ያለውን ክብርና የሚሰጠውን ጭማሪ ፀጋ፤
3. በአንፃሩም አላህን የማያመሰግን ደግሞ ካለው የሚቀነስበት ስለ መሆኑ፤
4. አላህ ፍፁም ሀብታምና የተብቃቃ ጌታ ስለ መሆኑ፤
5. ያለፉት ነብያት ታሪክና ያሣለፉትን የሕይወት ሂደት ማስታወስ አያሌ ጥቅሞችን የሚሰጥ አስተማሪ ታሪክ መሆኑን፤

وَبَرَزُوا۟ لِلَّهِ جَمِيعًا فَقَالَ ٱلضُّعَفَـٰٓؤُا۟ لِلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُوٓا۟ إِنَّا كُنَّا لَكُمْ تَبَعًا فَهَلْ أَنتُم مُّغْنُونَ
عَنَّا مِنْ عَذَابِ ٱللَّهِ مِن شَىْءٍ ۚ قَالُوا۟ لَوْ هَدَىٰنَا ٱللَّهُ لَهَدَيْنَـٰكُمْ ۖ سَوَآءٌ عَلَيْنَآ أَجَزِعْنَآ أَمْ
صَبَرْنَا مَا لَنَا مِن مَّحِيصٍ ﴿٢١﴾

**21.** የተሰበሰቡ ሆነው ለአላህ ይገልጻሉ (ይከለከላሉ) ሐሳበ ደካማዎቹም ተከታዮች ለእነዚያ ለኮሩት እኛ ለእናንተ ተከታዮች ነበርን እናንተ ከአላህ ቅጣት ከእኛ ላይ አንዳችን ነገር ተከላካዮች ናችሁን? ይሏቸዋል (አስከታዮችም)። አላህ ባቀናን ኖሮ በመራናችሁ ነበር ይሏቸዋል። ብንበሳጭ ወይም ብንታገሥም በእኛ ላይ እኩል ነው። ለእኛ ምንም መጠጊያ የለንም ይላሉ።

وَقَالَ ٱلشَّيْطَـٰنُ لَمَّا قُضِىَ ٱلْأَمْرُ إِنَّ ٱللَّهَ وَعَدَكُمْ وَعْدَ ٱلْحَقِّ وَوَعَدتُّكُمْ فَأَخْلَفْتُكُمْ ۖ
وَمَا كَانَ لِىَ عَلَيْكُم مِّن سُلْطَـٰنٍ إِلَّآ أَن دَعَوْتُكُمْ فَٱسْتَجَبْتُمْ لِى ۖ فَلَا تَلُومُونِى وَلُومُوٓا۟
أَنفُسَكُم ۖ مَّآ أَنَا۠ بِمُصْرِخِكُمْ وَمَآ أَنتُم بِمُصْرِخِىَّ ۖ إِنِّى كَفَرْتُ بِمَآ أَشْرَكْتُمُونِ مِن قَبْلُ ۗ
إِنَّ ٱلظَّـٰلِمِينَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٢٢﴾

**22.** ነገሩም በተፈፀመ ጊዜ ሰይጣን ይላቸዋል። አላህ እውነተኛውን ቃል ኪዳን ገባላችሁ እኔም ቃል ኪዳንም ገባሁላችሁ። አፈረስኩባችሁም። ለእኔም በእናንተ ላይ ምንም ሥልጣን አልነበረኝም። ግና ጠራኋችሁና ለኔም ታዘዛችሁኝ። ስለዚህ አትውቀሱኝ ነፍሶቻችሁንም ውቀሱ። እኔ የምረዳችሁ አይደለሁም እናንተም የምትረዱኝ አይደላችሁም እኔ ከአሁን በፊት ለአላህ ተጋሪ በአደረጋችሁት ነገር ሁሉ ካድኩ በዳዮቹ ሁሉ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

وَأُدْخِلَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ جَنَّـٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ خَـٰلِدِينَ فِيهَا
بِإِذْنِ رَبِّهِمْ ۖ تَحِيَّتُهُمْ فِيهَا سَلَـٰمٌ ﴿٢٣﴾

**23.** እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ሁሉ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ በጌታቸው ፈቃድ እንዲገቡ ይደረጋሉ። በውስጣቸው መከባበሪያቸው ሰላምታቸው ሰላም ለእናንተ ይሁን መባባል ነው።

أَلَمْ تَرَ كَيْفَ ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا كَلِمَةً طَيِّبَةً كَشَجَرَةٍ طَيِّبَةٍ أَصْلُهَا ثَابِتٌ وَفَرْعُهَا فِى ٱلسَّمَآءِ ﴿٢٤﴾
تُؤْتِىٓ أُكُلَهَا كُلَّ حِينٍۭ بِإِذْنِ رَبِّهَا ۗ وَيَضْرِبُ ٱللَّهُ ٱلْأَمْثَالَ لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ ﴿٢٥﴾ وَمَثَلُ
كَلِمَةٍ خَبِيثَةٍ كَشَجَرَةٍ خَبِيثَةٍ ٱجْتُثَّتْ مِن فَوْقِ ٱلْأَرْضِ مَا لَهَا مِن قَرَارٍ ﴿٢٦﴾

**24-26.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ መልካምን ቃል ሥሯ በምድር ውስጥ የተደላደለች ቅርንጫፏም ወደ ሰማይ የረዘመች እንደሆነች መልካም ዛፍ አድርጎ ምሳሌን እንዴት እንደገለፀ አላየህምን? ምግቧን (ፍሬዋን) በጌታዋ ፈቃድ በየጊዜው ትሰጣለች። አላህ ለሰዎች ይገሰፁ ዘንድ ምሳሌዎችን ይገልጻል። የመጥፎ ቃል ምሳሌ ከምድር በላይ የተገረሰሰች ለእርሷ ምንም መደላደል የሌላት እንደ ሆነች መጥፎ ዛፍ ነው።

يُثَبِّتُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱلْقَوْلِ ٱلثَّابِتِ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا وَفِى ٱلْـَٔاخِرَةِ ۖ
وَيُضِلُّ ٱللَّهُ ٱلظَّٰلِمِينَ ۚ وَيَفْعَلُ ٱللَّهُ مَا يَشَآءُ ﴿٢٧﴾

**27.** አላህ እነዚያን በትክክል በአላህ ያመኑትን በቅርቢቱም ህይወት ሆነ በመጨረሻይቱም (በመቃብር) በተረጋገጠው ቃል (በሸሀዳ) ላይ ያደርጋቸዋል (ያፀናቸዋል)። ከሓዲያን አላህ ያሳስታቸዋል አላህም የሚሻውን ይሰራልና።

۞ أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ بَدَّلُوا۟ نِعْمَتَ ٱللَّهِ كُفْرًا وَأَحَلُّوا۟ قَوْمَهُمْ دَارَ ٱلْبَوَارِ ﴿٢٨﴾
جَهَنَّمَ يَصْلَوْنَهَا ۖ وَبِئْسَ ٱلْقَرَارُ ﴿٢٩﴾ وَجَعَلُوا۟ لِلَّهِ أَندَادًا لِّيُضِلُّوا۟ عَن سَبِيلِهِۦ ۗ
قُلْ تَمَتَّعُوا۟ فَإِنَّ مَصِيرَكُمْ إِلَى ٱلنَّارِ ﴿٣٠﴾

**28-30.** ወደ እነዚያ የአላህን ፀጋ በክህደት ወደ ለወጡትና ህዝቦቻቸውን በጥፋት ሀገር ወዳሰፈሩት (ወደ ቁረይሾች) አላየህምን? (አልተመለከትክምን) ሀገሪቱም የሚገቡባት ስትሆን ገሀነም ናት። መርጊያነቷ ምንኛ ትከፋ፣ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለአላህ ከመንገዱ ያሳስቱ ዘንድ ባላንጣዎችን አደረጉለት። (ሙሐመድ ሆይ!)፣ ጥቂትን ተጠቀሙ መመለሻችሁም ወደ እሳት ነው በላቸው።

ከኢብራሂም ምዕራፍ (28) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በበድር ቀን በሞቱት ሙስሊሞች ምክንያት ነው የወረደው የሚለውን ቢዘግቡትም አንቀፁ ከመካዊ ምዕራፎች አንዱ በመሆኑ ብዙ ሰዎች አልተቀበሉትም። (ሱዩጢ)

**ከኢብራሂም ምዕራፍ ከአንቀፅ (21-30) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. እከሌን አምኜና ተከትዬ ነው ከትክክለኛው የእምነት ጎዳና የወጣሁት ይቅርታ ይደረግልኝ በሚል የሚቀርቡ ምክንያቶች በሙሉ ውድቅ እንደሚሆኑ፤
2. ከአላህ ውጭ ላሉ አካላት በሙሉ የሚደረጉ አምልኮቶች ሰይጣንን እንደማምለክ የሚቆጠሩ መሆናቸውን፤
3. አላህ ወደ ፊት የሚከሰቱትንና እስካሁን እውን ያልሆኑ ድርጊቶችን በሙሉ አስቀድሞ የሚያውቃቸው ስለመሆኑ፤
4. መልካም ስራ መግቢያ ለጀነት እንደ መነሻ ምክንያት ይሆናል እንጂ ዋነኛ ምክንያት እንደማይሆን፤
5. ትምህርትን በሰዎች ልብ ውስጥ ለማስረፅ ሲባል ምሳሌዎችን እየሳሉ ማስተማር ጥሩ የማስተማር ዘዴ መሆኑን፤
6. ከህደትና እምነት ያላቸውን ልዩነት ማነፃፀር፤
7. አንድ ሙዕሚን ኢማኑን ጠብቆ በፅናት እንደኖረው ሁሉ ኢማኑን ጠብቆ ሊሞት እንደሚገባ እንማራለን።

قُل لِّعِبَادِيَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ يُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُنفِقُواْ مِمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡ سِرّٗا وَعَلَانِيَةٗ مِّن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَ يَوۡمٞ لَّا بَيۡعٞ فِيهِ وَلَا خِلَٰلٌ ﴿٣١﴾

**31.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፣ ለእነዚያ ላመኑት ባሮቼ በእርሱ ውስጥ ሽያጭና ወዳጅነት የሌለበት ቀን ከመምጣቱ በፊት ሶላትን በደንቡ ስገዱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ በሚስጢርም ሆነ በግልጽ ለግሱም በላቸው።

ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجَ بِهِۦ مِنَ ٱلثَّمَرَٰتِ رِزۡقٗا لَّكُمۡۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡفُلۡكَ لِتَجۡرِيَ فِي ٱلۡبَحۡرِ بِأَمۡرِهِۦۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلۡأَنۡهَٰرَ ﴿٣٢﴾ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ دَآئِبَيۡنِۖ وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ ﴿٣٣﴾ وَءَاتَىٰكُم مِّن كُلِّ مَا سَأَلۡتُمُوهُۚ وَإِن تَعُدُّواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ لَا تُحۡصُوهَآۗ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَظَلُومٞ كَفَّارٞ ﴿٣٤﴾

**32-34.** አላህ ያ! ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ከሰማይ ዳመናም ውሃን ያወረደናም በእርሱ ከፍሬዎች ሁሉ ለእናንተ ሲሳይን ያወጣላችሁ መርከቦችንም በፈቃዱ በባህር ላይ ይንሳፈፉ ዘንድ ለእናንተ ያገራ፤ ወንዞችንም ለናንተ ያገራ ነው። ፀሓይንና ጨረቃንም ዘወትር ሒያጆች ሲሆኑ ለእናንተ የገራ ሌሊትንና ቀንንም ለእናንተ የገራላችሁ ነው። ከለመናችሁት ሁሉ የሰጣችሁ ነው። የአላህን ፀጋ ብትቆጥሩ አትዘልቁትም። ሰው በጣም በደለኛ ከሓዲ ነው።

وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ رَبِّ ٱجۡعَلۡ هَٰذَا ٱلۡبَلَدَ ءَامِنٗا وَٱجۡنُبۡنِي وَبَنِيَّ أَن نَّعۡبُدَ ٱلۡأَصۡنَامَ ٣٥
رَبِّ إِنَّهُنَّ أَضۡلَلۡنَ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلنَّاسِۖ فَمَن تَبِعَنِي فَإِنَّهُۥ مِنِّيۖ وَمَنۡ عَصَانِي فَإِنَّكَ غَفُورٞ
رَّحِيمٞ ٣٦ رَّبَّنَآ إِنِّيٓ أَسۡكَنتُ مِن ذُرِّيَّتِي بِوَادٍ غَيۡرِ ذِي زَرۡعٍ عِندَ بَيۡتِكَ ٱلۡمُحَرَّمِ رَبَّنَا
لِيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ فَٱجۡعَلۡ أَفۡـِٔدَةٗ مِّنَ ٱلنَّاسِ تَهۡوِيٓ إِلَيۡهِمۡ وَٱرۡزُقۡهُم مِّنَ ٱلثَّمَرَٰتِ لَعَلَّهُمۡ
يَشۡكُرُونَ ٣٧ رَبَّنَآ إِنَّكَ تَعۡلَمُ مَا نُخۡفِي وَمَا نُعۡلِنُۗ وَمَا يَخۡفَىٰ عَلَى ٱللَّهِ مِن شَيۡءٖ فِي ٱلۡأَرۡضِ
وَلَا فِي ٱلسَّمَآءِ ٣٨ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِي وَهَبَ لِي عَلَى ٱلۡكِبَرِ إِسۡمَٰعِيلَ وَإِسۡحَٰقَۚ إِنَّ رَبِّي لَسَمِيعُ
ٱلدُّعَآءِ ٣٩ رَبِّ ٱجۡعَلۡنِي مُقِيمَ ٱلصَّلَوٰةِ وَمِن ذُرِّيَّتِيۚ رَبَّنَا وَتَقَبَّلۡ دُعَآءِ ٤٠ رَبَّنَا ٱغۡفِرۡ لِي
وَلِوَٰلِدَيَّ وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلۡحِسَابُ ٤١

**35-41.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂም ባለ ጊዜ (አስታውስ)። ጌታዬ ሆይ፣ ይህንን አገር መካን ፀጥተኛ አድርገው። እኔንና ልጆቼንም ጣኦታትን ከመገዛት አርቀን። ጌታዬ ሆይ፣ እነርሱ ጣኦታት ከሰዎች ብዙዎችን አሳስተዋልና። የተከተለኝም ሰው እርሱ ከእኔ ነው። ትዕዛዜን የጣሰ ሰው ግን አንተ መሓሪና አዛኝ ነህ። ጌታችን ሆይ፣ እኔ አዝመራ በሌለው ሸለቆ ውስጥ በተከበረው ቤት በካዕባ አጠገብ ከዘሮቼ አስቀመጥኩ። ጌታችን ሆይ! ሶላትን ደንቡን ጠብቀው ይሰግዱ ዘንድ አስቀመጥኳቸው። ከሰዎችም ልቦችን ወደ እነርሱ የሚናፍቁ አድርግ። ያመሰግኑህም ዘንድ ከፍሬዎች ስጣቸው። ጌታችን ሆይ፣ አንተ የምንደብቀውንም የምንገልፀውንም ሁሉ ጠንቅቀህ ታውቃለህ። በአላህ ላይ በምድርም በሰማይም ምንም ነገር አይደበቅም። ለእዚያ ከሽምግልና በኋላ ኢስማኢልንና ኢስሐቅን ለሰጠኝ አላህ ምስጋና ሁሉ ይገባው ጌታዬ ልመናን ሰሚ ነውና። ጌታዬ ሆይ፣ ሶላትን አዘውትሬ የምሰግድ አድርገኝ። ከዘሮቼም አድርግ ጌታዬ ሆይ፣ ፀሎቴንም ተቀበለኝ። ጌታችን ሆይ፣ ለእኔም ለወላጆቼም ለምዕመናንም ሁሉ ምርመራ በሚደረግበት ቀን ማረን።

وَلَا تَحۡسَبَنَّ ٱللَّهَ غَٰفِلًا عَمَّا يَعۡمَلُ ٱلظَّٰلِمُونَۚ إِنَّمَا يُؤَخِّرُهُمۡ لِيَوۡمٖ تَشۡخَصُ فِيهِ
ٱلۡأَبۡصَٰرُ ٤٢ مُهۡطِعِينَ مُقۡنِعِي رُءُوسِهِمۡ لَا يَرۡتَدُّ إِلَيۡهِمۡ طَرۡفُهُمۡۖ وَأَفۡـِٔدَتُهُمۡ هَوَآءٞ ٤٣ وَأَنذِرِ
ٱلنَّاسَ يَوۡمَ يَأۡتِيهِمُ ٱلۡعَذَابُ فَيَقُولُ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ رَبَّنَآ أَخِّرۡنَآ إِلَىٰٓ أَجَلٖ قَرِيبٖ نُّجِبۡ
دَعۡوَتَكَ وَنَتَّبِعِ ٱلرُّسُلَۗ أَوَلَمۡ تَكُونُوٓاْ أَقۡسَمۡتُم مِّن قَبۡلُ مَا لَكُم مِّن زَوَالٖ ٤٤

**42-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህን በደለኞች ከሚሠሩት ግፍ ዘንጊ አድርገህ አታስብ የሚያቆያቸው ዓይኖች በእርሱ እስከሚፈጡበት ቀን ድረስ ብቻ ነው። ወደ ጠሪው መልአክ ቸኳዮች ራሶቻቸውን አንጋጣጮች ሆነው ዓይኖቻቸው ይፈጣሉ ዓይኖቻቸው ወደ እነርሱ አይመለሱም። ልቦቻቸው ባዶዎች ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎችን ቅጣቱ የሚመጣባቸውን ቀን አስፈራራቸው። እነዚያ የበደሉትማ ጌታችን ሆይ! እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አቆየን። ጥሪህን እንቀበላለንና መልዕክተኞቹንም እንከተላለንና ይላሉ። ከአሁን በፊት በምድረ ዓለም ለእናንተ ምንም መወገድ የላችሁም በማለት የማላችሁ አልነበራችሁምን? ይባላሉ።

وَسَكَنتُمْ فِي مَسَٰكِنِ ٱلَّذِينَ ظَلَمُوٓاْ أَنفُسَهُمْ وَتَبَيَّنَ لَكُمْ كَيْفَ فَعَلْنَا بِهِمْ وَضَرَبْنَا
لَكُمُ ٱلْأَمْثَالَ ﴿٤٥﴾ وَقَدْ مَكَرُواْ مَكْرَهُمْ وَعِندَ ٱللَّهِ مَكْرُهُمْ وَإِن كَانَ مَكْرُهُمْ لِتَزُولَ مِنْهُ
ٱلْجِبَالُ ﴿٤٦﴾ فَلَا تَحْسَبَنَّ ٱللَّهَ مُخْلِفَ وَعْدِهِۦ رُسُلَهُۥٓ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ ذُو ٱنتِقَامٍ ﴿٤٧﴾

**45-47.** በእነዚያ ነፍሶቻቸውን በበደሉት ሰዎች መኖሪያ*1 ውስጥ ተቀመጣችሁ። በእነርሱም እንዴት እንደሠራንባቸው ለእናንተ ተገለፀላችሁ ለእናንተ ምሳሌዎችን ገለጽንላችሁ። (በነብዩ ላይ) ሴራቸውን አሴሩ። ሴራቸውም ቅጣቱ አላህ ዘንድ ነው። ሴራቸውም ኮረብታዎች በእርሱ የሚወገዱበት አልነበረም*2። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህን ለመልዕክተኞቹ የገባላቸውን ቃል ኪዳኑን አፍራሽ አድርገህ አታስብ። አላህ አሸናፊ፣ የመበቀል ባለቤት ነው።

*1 ይህን ቦታ በሳውዲ አረቢያ ውስጥ ከሚገኙ በሰሜኑ ክፍለ ሀገራት መካከል ተቡክ ከሚባለው ከሚባለውና ዑላ በሚባሉ አገሮች አካባቢ ላይ የነበረ የነብዩ ሷሊህ ሰፈር ነው የሚለው በኡለማዎች ዘንድ ተመረጧል።

*2 ሴራቸው ጋራን ለማፍረስ የሚቀርብ ቢሆንም እንኳን ተብሎም ሊተረጎም ይችላል።

يَوْمَ تُبَدَّلُ ٱلْأَرْضُ غَيْرَ ٱلْأَرْضِ وَٱلسَّمَٰوَٰتُ ۖ وَبَرَزُواْ لِلَّهِ ٱلْوَٰحِدِ ٱلْقَهَّارِ ﴿٤٨﴾ وَتَرَى
ٱلْمُجْرِمِينَ يَوْمَئِذٍ مُّقَرَّنِينَ فِي ٱلْأَصْفَادِ ﴿٤٩﴾ سَرَابِيلُهُم مِّن قَطِرَانٍ وَتَغْشَىٰ وُجُوهَهُمُ
ٱلنَّارُ ﴿٥٠﴾ لِيَجْزِيَ ٱللَّهُ كُلَّ نَفْسٍ مَّا كَسَبَتْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَرِيعُ ٱلْحِسَابِ ﴿٥١﴾

**48-51.** ምድር በሌላ ምድር የምትለወጥበትን ሰማያትም እንደዚሁ በሌላ ሰማያት የሚለወጥበትን እና አንድ ብቸኛና አሸናፊ ለሆነው አላህ ፍጡራን ሁሉ የሚገለፁበትን ቀን (የሚሆነውን አስታውስ)። (መልዕክተኛችን

ሙሐመድ ሆይ)፣ አመፀኞችን በዚያ ቀን በሰንሰለቶች ተቆራኝተው ታያቸዋለህ። ቀሚሶቻቸው ከካትራም የተሰሩ ናቸው። ፊቶቻቸውንም እሳት ትሸፍናቸዋለች። አላህ (ይህንን ያደረገው) ነፍስ ሁሉ የሠራችውን ይመነዳ ዘንድ ነው። አላህ ምርመራው ፈጣን ነው።

هَٰذَا بَلَٰغٌ لِّلنَّاسِ وَلِيُنذَرُواْ بِهِۦ وَلِيَعۡلَمُوٓاْ أَنَّمَا هُوَ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞ وَلِيَذَّكَّرَ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ﴿٥٢﴾

**52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ (ቁርኣን) ለሰዎች ገሳጭና መድረስ ያለበት ነው። ሊመከሩበት በርሱ ሊስፈራሩበት፤ እርሱም አንድ አምላክ ብቻ መሆኑን ሊያውቁበት፤ የአእምሮ ባለቤቶችም ሊገሰፁበት የተወረደ ነው።

**ከኢብራሂም ምዕራፍ ከ (31-52) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሶላት አስተካክሎ መስገድ፤ ዘካንም መክፈል ግዴታ ስለ መሆኑ፤
2. ሰደቃን በይፋ መስጠትም ሆነ በድብቅ መለገስ እኩልና መልካም ተግባር መሆኑን፤
3. አምልኮ የሚገባው ለአላህ ብቻ መሆኑንና ከአላህ ሌላ ማምለክ እጅግ የተወገዘ ወንጀል ስለ መሆኑ፤
4. የሰው ልጅ ኢስላምን በአግባቡ ጠብቆ ተግባራዊ ካላደረገ የግፍ አራማጅ እንደሆነና ግፈኛ ተብሎ እንደሚሰየም፤
5. መካ የተከበረ የአላህ ቤት መሆኑን፤
6. እምነትን መሠረት ያደረጉ ግንኙነቶች በሙሉ በሌላ መንገድ ከሚፈጠሩ ግንኙነቶች በሙሉ የተሻሉና ጠንካራ መሠረት እንደሚኖራቸው፤
7. ሶላት ክብደት ያለው የኢስላም መሠረታዊ ትዕዛዝ ስለመሆኑ፤
8. ነብዩ ኢብራሒም ያደረጉት ዱዓ ከአላህ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱን፤
9. አላህ ለዋለልን መጠነ ሰፊ ውለታ ምስጋና ማቅረብ የሚገባን ስለመሆኑ፤
10. ለራስም ሆነ ለመላው ምዕመናን ምህረት መጠየቁ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
11. ከሞት በኋላ ደግሞ ሕይወት መኖሩ የማይቀር ሃቅ መሆኑን፤
12. ግፈኞች የአላህ ቅጣት የማያገኛቸው አላህ ዘንግቷቸው አልያም ቅጣት እንዳያገኛቸው አድርጎ ትቷቸው ሣይሆን ጊዜ እየጠበቀላቸው ስለመሆኑ፤
13. የቂያማ ቀን አስደንጋጭ የሆኑ ክስተቶች የሚታዩበት ቀን መሆኑን ማስታወስ፤
14. የቁረይሽ ጣዖታዊያን ተንኮል ምን ያህል የከፋ ደረጃ ደርሶ እንደነበር እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የኢብራሂም ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (15)
# የሒጅር ሰዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሒጅር)

سُورَةُ الحِجْرِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (99) ናቸው።
### የሱረቱ አል ሒጅር መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በወረደበት አመት ነብዩ (ﷺ) በጣም ተጨንቀው የነበሩበት የሐዘን አመት ነበር። ምክንያቱም የነብዩ (ﷺ) ደጋፊዎች የነበሩት ማለትም በገንዘባቸውና በህይወታቸው ከነብዩ (ﷺ) ጎን የነበሩት ውድ ባለቤታቸው ኸዲጃና እምነቱን ባይቀበሉም ማንም አይነካህም በማለት ከጎናቸው ቆመው የነበሩት አጎታቸው አቡጧሊብ በአንድ ሰሞን ተከታትለው አንዳንድ የታሪክ ሰዎች እንደሚሉት በሶስት ቀናት ልዩነት የሞቱበት ዘመን ስለነበር ነው። በግዜው ከነበረው ችግርና ውጥረት ከዚያ ጋር እምነትን ፈታኝ የሆነው የኢስራእ ጉዞ መከሰት ተጨማምሮበት አንዳንድ ሰዎች እምነታቸው ላይ በመጠራጠር ላይ የነበሩበት አመት ነበር። ለዚህም ይመስላል ትኩረቱን በአብዛሀኛው ነብዩን (ﷺ) በማበረታታትና በማፅናናት ችግሮችን በትዕግስት ማለፍ እንዳለባቸው በማጠናከር ላይ ያተኮረው ይህን ሁሉ ሊያደርግ የሚችለውን የኃያሉን አላህ ችሎታና ጥበብ በሰፊው ይዘረዝራል። የሰው ልጆችን ታሪክ ነካክቶ በመጨረሻም የከሓዲያን አመፅና የጥፋታቸውን ምክንያት ከጠቀሰ በኋላ ሙቶ መነሳት አይቀሬ ሐቅ መሆኑን ያሰምርበታል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓرۚ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِ وَقُرۡءَانٖ مُّبِينٖ ١

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ራ፤* (በእነዚህ ፊደሎች ምን እንደፈለገ አላህ ራሱ ብቻ ያውቃል)። እኒህ አንቀፆች ከመጽሐፍ አንቀፆችና ገላጭ ከሆነው ቁርኣን ናቸው።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፤ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

رُّبَمَا يَوَدُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَوۡ كَانُواْ مُسۡلِمِينَ ٢ ذَرۡهُمۡ يَأۡكُلُواْ وَيَتَمَتَّعُواْ وَيُلۡهِهِمُ ٱلۡأَمَلُۖ
فَسَوۡفَ يَعۡلَمُونَ ٣ وَمَآ أَهۡلَكۡنَا مِن قَرۡيَةٍ إِلَّا وَلَهَا كِتَابٞ مَّعۡلُومٞ ٤ مَّا تَسۡبِقُ مِنۡ أُمَّةٍ
أَجَلَهَا وَمَا يَسۡتَـٔۡخِرُونَ ٥

**2-5.** እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች (በትንሳኤ ቀን) ሙስሊሞች በሆንን ኖሮ ብለው በብዛት ይመኛሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱን ተዋቸው። ይብሉ ይጠቀሙም። ተስፋም ያዘናጋቸው። በእርግጥም (መጥፎ ፍጻሜያቸውን) ያውቃሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ማንኛይቱንም ከተማ ለእርሷ የተወሰነ መጽሐፍ ጊዜያት ያላት ሆና እንጂ አላጠፋንም። ማንኛይቱም ሕዝብ የመጥፊያ ጊዜዋን በምንም ዘዴ አትቀድምም። ከእርሱም በማንም ሀይል አትቆይምም።

وَقَالُواْ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِي نُزِّلَ عَلَيۡهِ ٱلذِّكۡرُ إِنَّكَ لَمَجۡنُونٞ ٦
لَّوۡمَا تَأۡتِينَا بِٱلۡمَلَـٰٓئِكَةِ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّـٰدِقِينَ ٧

**6-7.** የመካ ከሓዲያን አንተ ያ! በእርሱ ላይ ቁርኣን የተወረደለት ሆይ! አንተ በእርግጥ እብድ ነህ አሉ። ከእውነተኞቹ እንደ ሆንክ መስካሪ መላዕክት ለምን አታመጣም አሉ።

مَا نُنَزِّلُ ٱلۡمَلَـٰٓئِكَةَ إِلَّا بِٱلۡحَقِّ وَمَا كَانُوٓاْ إِذٗا مُّنظَرِينَ ٨
إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا ٱلذِّكۡرَ وَإِنَّا لَهُۥ لَحَٰفِظُونَ ٩

**8-9.** መልአክትን ደግሞ በእውነት በቅጣት እንጂ አናወርድም። ያን ጊዜም የሚቆዩ ጊዜ የሚሰጣቸው አይደሉም። እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው። እኛው ብቻ ጠባቂዎቹ* ነን።

* ቁርኣን የሚጠበቀው በአላህ ለመሆኑ ከወረደበት ዘመን አንስቶ እስካሁን አንድም ቦታ ላይ መበረዝ አለመቻሉ በቂ ማስረጃ ነው። ማንም ሊጨምርበት ሊቀንስበት አይችልም። በ (41-42) ኛው ያሉት አናቅፅ ይህንኑ የቁርኣን አንቀፅ መልዕክት ያጠቃልላሉ። ቀደምት መፅሐፍቶች ሁሉም ከቁርኣን መውረድ በፊት ተበርዘዋል።

ለእነዚህ መፅሐፍት መበረዝ ዋናውና ትልቁ ምክንያት ለመፅሐፍቱ ጥበቃ በአላህ ቃል ኪዳን አለመግባቱ ነው። አላህ መፅሐፍቱን ሲያወርድ ጠብቁ ያለው ለነብያቶችና ለተከታዮቻቸው ነበር። «እኛ ተውራትን በውስጥዋ መመሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን ...» አል-ማኢዳህ (44) ኛው አንቀፅ ቁርኣን ደግሞ እስከ ዛሬ ድረስ ቅንጣት ታህል ሳይበረዝ የቆየበት ዋናውና ትልቁ ምክንያት መፅሐፉን ለመጠበቅ ሀላፊነቱን የወሰደው ራሱ አላህ ስለሆነ ነው፡- "እኛ ቁርኣንን እኛው አወረድነው፤» አል-ሂጅር. ም. (9) ኛው አንቀፅ፤ አል-ፉሲለት. ምዕራፍ. (42) ኛው አንቀፅ ለዚህም ዋናው ምክንያት ከቁርኣን በፊት የነበሩት ነብያት በተከታታይ ይላኩ ስለነበር ኋለኛው ነብይ ሊገልፅላቸው ይችል ነበር። ከቁርኣንና ከነብዩ (ﷺ) በኋላ ግን የሚላክ ነብይም ሆነ የሚወርድ ሌላ መፅሐፍ ስለሌለ አላህ ደግሞ በፍጡራት ላይ ማስረጃውን ካላቆመ ስለማይቀጣ መፅሐፉም እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ እንደጠበቅ ሀላፊነቱን ራሱ ወሰደ።

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ فِي شِيَعِ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٠ وَمَا يَأۡتِيهِم مِّن رَّسُولٍ إِلَّا كَانُواْ بِهِۦ
يَسۡتَهۡزِءُونَ ١١ كَذَٰلِكَ نَسۡلُكُهُۥ فِي قُلُوبِ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ١٢ لَا يُؤۡمِنُونَ بِهِۦ وَقَدۡ خَلَتۡ
سُنَّةُ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٣ وَلَوۡ فَتَحۡنَا عَلَيۡهِم بَابٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ فَظَلُّواْ فِيهِ يَعۡرُجُونَ ١٤ لَقَالُوٓاْ إِنَّمَا
سُكِّرَتۡ أَبۡصَٰرُنَا بَلۡ نَحۡنُ قَوۡمٞ مَّسۡحُورُونَ ١٥

**10-15.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተም በፊት በነበሩት በመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች ውስጥ (መልክተኞችን) በእርግጥ ልከናል። ማንኛውም መልዕክተኛ በእርሱ የሚያላግጡበት ሆነው እንጂ አይመጣላቸውም ነበር። እንደዚሁ ማስተባበልን በአመፀኞች ልቦች ውስጥ እናስገባዋለን። በእርሱ አያምኑበትም የቀድሞዎቹም ድርጊት በእርግጥ አልፋለች (እንደጠፉ ይጠፋሉ)። በእነርሱ ላይ ከሰማይ ደጃፍን በከፈትንላቸውና በእርሱ ሲወጡ ቢውሉም የተዘጉ ዓይኖቻችን ተጭበርብረው ነው። እንዲያውም እኛ የተደገመብን ሰዎች ነን ባሉ ነበር።

وَلَقَدۡ جَعَلۡنَا فِي ٱلسَّمَآءِ بُرُوجٗا وَزَيَّنَّٰهَا لِلنَّٰظِرِينَ ١٦ وَحَفِظۡنَٰهَا مِن كُلِّ شَيۡطَٰنٖ
رَّجِيمٍ ١٧ إِلَّا مَنِ ٱسۡتَرَقَ ٱلسَّمۡعَ فَأَتۡبَعَهُۥ شِهَابٞ مُّبِينٞ ١٨

**16-18.** በሰማይም ላይ ከዋክብቶችን* (ቡሩጆችን) በርግጥ አድርገናል (ፈጥረናል)፡፡ ለተመልካቾችም በከዋክብት አጊጠናታል፡፡ ከተባረረ ሰይጣንም ሁሉ ጠብቀናታል፡፡ ግን ወሬ መስማትን የሚሰርቅ ወዲያውኑ አብሪ ችቦ ይከተለዋል፡፡ (ያቃጥለዋል)፡፡

*✷ እነርሱም አስራ ሁለት ከዋክብት ናቸው፡፡ እነርሱንም ማወቅ ለብዙ ነገሮች ይጠቅማል፡፡ መንገዶችንና ሰዓትን ለማወቅ ይረዳል፡፡ እነርሱም ሀመል፤ ሰውር ጀውዛዕ፤ ሰረጣን፤ አሰድ፤ ሱንቡለህ፤ ሚዛን፤ ዐቅረብ፤ ቀውስ፤ ጁደይ፤ ደልውና ሁት ናቸው፡፡ ሰባት ተደጋጋሚ አናቅፅን ማለት ሁኖ በዚህም የተፈለገው የመግቢያዋን ነው፡፡*

وَٱلۡأَرۡضَ مَدَدۡنَٰهَا وَأَلۡقَيۡنَا فِيهَا رَوَٰسِيَ وَأَنۢبَتۡنَا فِيهَا مِن كُلِّ شَيۡءٖ مَّوۡزُونٖ ١٩ وَجَعَلۡنَا
لَكُمۡ فِيهَا مَعَٰيِشَ وَمَن لَّسۡتُمۡ لَهُۥ بِرَٰزِقِينَ ٢٠ وَإِن مِّن شَيۡءٍ إِلَّا عِندَنَا خَزَآئِنُهُۥ وَمَا
نُنَزِّلُهُۥٓ إِلَّا بِقَدَرٖ مَّعۡلُومٖ ٢١ وَأَرۡسَلۡنَا ٱلرِّيَٰحَ لَوَٰقِحَ فَأَنزَلۡنَا مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَسۡقَيۡنَٰكُمُوهُ
وَمَآ أَنتُمۡ لَهُۥ بِخَٰزِنِينَ ٢٢ وَإِنَّا لَنَحۡنُ نُحۡيِۦ وَنُمِيتُ وَنَحۡنُ ٱلۡوَٰرِثُونَ ٢٣

**19-23.** ምድርንም ዘረጋናት፡፡ በውስጧም ኮረብታዎችን ጣልንባት፡፡ በውስጧም የተለካን በቃይ ሁሉ አበቀልንባት፡፡ በእርሷ ውስጥ ለእናንተ ልዩ ልዩ መኖሪያዎችንና ለእርሱ መጋቢዎቹ ያልሆናችሁትንም እንስሳትን አደረግንላችሁ፡፡ መጋዘኖቹም መክፈቻቸው እኛ ዘንድ ያልሆነ ምንም ነገር የለም፡፡ በተወሰነም ልክ እንጂ አናወርደውም፡፡ ንፋስን ደመናን ተሸካሚዎች አድርገን ላክን፡፡ ከሰማይም ከደመና ዝናምን አወረድን፡፡ እርሱንም አጠጣናችሁ፡፡ እናንተ ለእርሱ አድላቢዎች አይደላችሁም፡፡ እኛ ሕያው የምናደርግና የምንገድል* እኛው ብቻ ነን፡፡ እኛው ፍጡርን ሁሉ የምንወርስ (ቀሪ) ነን፡፡

*✷ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ ሰው ሲሞት ሶስት ስራዎቹ ብቻ ሲቀሩ ሌሎቹ ይቋረጣሉ፡፡ እነሱም (1) ቀጣይነት ያለው ልገሳ፤ (2) ሰዎች የሚጠቀሙበት እውቀት፤ (3) ዱዓእ የሚያደርግ መልካም ልጅ ያለው፡፡»*

وَلَقَدۡ عَلِمۡنَا ٱلۡمُسۡتَقۡدِمِينَ مِنكُمۡ وَلَقَدۡ عَلِمۡنَا ٱلۡمُسۡتَـٔۡخِرِينَ ٢٤
وَإِنَّ رَبَّكَ هُوَ يَحۡشُرُهُمۡۚ إِنَّهُۥ حَكِيمٌ عَلِيمٞ ٢٥

**24-25.** ከናንተም ተቀዳሚዎቹን በእርግጥ አውቀናል፡፡ ወደ ኋላ ቀሪዎቹንም በእርግጥ አውቀናል፡፡ ጌታህ እርሱ ይሰበስባቸዋል፡፡ እርሱ ጥበበኛና ዐዋቂ ነውና፡፡

وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ مِن صَلْصَٰلٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ ﴿٢٦﴾ وَٱلْجَآنَّ خَلَقْنَٰهُ مِن قَبْلُ مِن نَّارِ
ٱلسَّمُومِ ﴿٢٧﴾ وَإِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّى خَٰلِقٌۢ بَشَرًا مِّن صَلْصَٰلٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ ﴿٢٨﴾
فَإِذَا سَوَّيْتُهُۥ وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن رُّوحِى فَقَعُوا۟ لَهُۥ سَٰجِدِينَ ﴿٢٩﴾ فَسَجَدَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ كُلُّهُمْ
أَجْمَعُونَ ﴿٣٠﴾ إِلَّآ إِبْلِيسَ أَبَىٰٓ أَن يَكُونَ مَعَ ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿٣١﴾

**26-31.** ሰውንም ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጥቁር ጭቃ በእርግጥ ፈጠርነው። ጃንንም (የጅኖች አባት) ከሰው በፊት ከእሳት ነበልባል ፈጠርነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም ለመላዕክት ባለ ጊዜ የሆነውን አስታውስ። እኔ ሰውን ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከሚገማ ጭቃ እፈጥራለሁ። ፍጥረቱን ባስተካከልኩትና በውስጡ ከመንፈሴ በነፋሁበትም ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ሆናችሁ ውደቁ። መላእክትም ሁሉም ተሰብስበው ሰገዱ። ኢብሊስ (ዲያብሎስ) ብቻ ሲቀር ከሰጋጆቹ ጋር ከመሆን እንቢ አለ።

قَالَ يَٰٓإِبْلِيسُ مَا لَكَ أَلَّا تَكُونَ مَعَ ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿٣٢﴾ قَالَ لَمْ أَكُن لِّأَسْجُدَ لِبَشَرٍ خَلَقْتَهُۥ
مِن صَلْصَٰلٍ مِّنْ حَمَإٍ مَّسْنُونٍ ﴿٣٣﴾ قَالَ فَٱخْرُجْ مِنْهَا فَإِنَّكَ رَجِيمٌ ﴿٣٤﴾ وَإِنَّ عَلَيْكَ ٱللَّعْنَةَ
إِلَىٰ يَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٣٥﴾ قَالَ رَبِّ فَأَنظِرْنِىٓ إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ ﴿٣٦﴾ قَالَ فَإِنَّكَ مِنَ ٱلْمُنظَرِينَ ﴿٣٧﴾
إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْوَقْتِ ٱلْمَعْلُومِ ﴿٣٨﴾ قَالَ رَبِّ بِمَآ أَغْوَيْتَنِى لَأُزَيِّنَنَّ لَهُمْ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَأُغْوِيَنَّهُمْ
أَجْمَعِينَ ﴿٣٩﴾ إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ ٱلْمُخْلَصِينَ ﴿٤٠﴾ قَالَ هَٰذَا صِرَٰطٌ عَلَىَّ مُسْتَقِيمٌ ﴿٤١﴾ إِنَّ
عِبَادِى لَيْسَ لَكَ عَلَيْهِمْ سُلْطَٰنٌ إِلَّا مَنِ ٱتَّبَعَكَ مِنَ ٱلْغَاوِينَ ﴿٤٢﴾ وَإِنَّ جَهَنَّمَ لَمَوْعِدُهُمْ
أَجْمَعِينَ ﴿٤٣﴾ لَهَا سَبْعَةُ أَبْوَٰبٍ لِّكُلِّ بَابٍ مِّنْهُمْ جُزْءٌ مَّقْسُومٌ ﴿٤٤﴾

**32-44.** (አላህም)፡ ኢብሊስ ሆይ! ከሰጋጆቹ ጋር የማትሆን ላንተ ምን ምክንያት አላህ አለው። ከሚቅጨለጨል ሸክላ ከግም ጭቃ ለፈጠርከው ሰው ልሰግድ አይገባኝም አለ። አላህ አለው። ከእርሷም ውጣ አንተ የተባረርክ እርጉም ነህና። በአንተ ላይም እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ እርግማን አለብህ። ጌታዬ ሆይ፣ እንግዲያውስ (ሰዎች) እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ አቆየኝ አለ። አላህም አለ፡- አንተ ከሚቆዩት ነህ። እስከታወቀው ወቅት ቀን ድረስ። ኢብሊስም አለ፡- ጌታዬ ሆይ! እኔን በማጥመምህ ይሁንብኝ ለእነርሱ በምድር ላይ ኃጢአትን እሸልምላቸዋለሁ። ሁላቸውንም አጠማቸዋለሁ አለ። ከእነርሱ

ፍፁሞቹ ባሮችህ ብቻ ሲቀሩ፡፡ አላህም አለ፡- ይህ በእኔ ላይ መጠበቁ የተገባ ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡ እነሆ ባሮቼ! በእነርሱ ላይ አንተ ስልጣን የለህም፡፡ ከጠማሞች የተከተለህ ሰው ብቻ ሲቀር፡፡ ገሀነምም ለእርሱና ለተከተሉት ለሁሉም በእርግጥ ቀጠሯቸው ናት፡፡ ለእርሷ ሰባት በሮች አሏት፡፡ ለየበሮቹም ሁሉ ከሰይጣናት ጭፍሮች የተከፋፈለ ድርሻ አለ፡፡

إِنَّ ٱلۡمُتَّقِينَ فِي جَنَّٰتٖ وَعُيُونٍ ﴿٤٥﴾ ٱدۡخُلُوهَا بِسَلَٰمٍ ءَامِنِينَ ﴿٤٦﴾ وَنَزَعۡنَا مَا فِي صُدُورِهِم مِّنۡ
غِلٍّ إِخۡوَٰنًا عَلَىٰ سُرُرٖ مُّتَقَٰبِلِينَ ﴿٤٧﴾ لَا يَمَسُّهُمۡ فِيهَا نَصَبٞ وَمَا هُم مِّنۡهَا بِمُخۡرَجِينَ ﴿٤٨﴾
۞ نَبِّئۡ عِبَادِيٓ أَنِّيٓ أَنَا ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٤٩﴾ وَأَنَّ عَذَابِي هُوَ ٱلۡعَذَابُ ٱلۡأَلِيمُ ﴿٥٠﴾

**45-50.** እነዚያ ከኃጢአት የተጠነቀቁት በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው፡፡ ፀጥተኞች ሆናችሁ በሰላም ግቧት (ይባላሉ)፡፡ በአልጋዎችም ላይ ፊት ለፊት የሚተያዩ ወንድማማቾች ሆነው በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ቂም ሁሉ እናስወግዳለን፡፡ በእርሷም ውስጥ ድካም አይነካቸውም እነርሱም ከእርሷ የሚወጡ አይደሉም፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መሐሪ፣ አዛኝ እኔው ብቻ መሆኔን ለባሮቼ ንገራቸው፡፡ ቅጣቴም አሳማሚ ቅጣት መሆኑን (ንገራቸው)፡፡

وَنَبِّئۡهُمۡ عَن ضَيۡفِ إِبۡرَٰهِيمَ ﴿٥١﴾ إِذۡ دَخَلُواْ عَلَيۡهِ فَقَالُواْ سَلَٰمٗا قَالَ إِنَّا مِنكُمۡ وَجِلُونَ ﴿٥٢﴾
قَالُواْ لَا تَوۡجَلۡ إِنَّا نُبَشِّرُكَ بِغُلَٰمٍ عَلِيمٖ ﴿٥٣﴾ قَالَ أَبَشَّرۡتُمُونِي عَلَىٰٓ أَن مَّسَّنِيَ ٱلۡكِبَرُ فَبِمَ
تُبَشِّرُونَ ﴿٥٤﴾ قَالُواْ بَشَّرۡنَٰكَ بِٱلۡحَقِّ فَلَا تَكُن مِّنَ ٱلۡقَٰنِطِينَ ﴿٥٥﴾ قَالَ وَمَن يَقۡنَطُ مِن
رَّحۡمَةِ رَبِّهِۦٓ إِلَّا ٱلضَّآلُّونَ ﴿٥٦﴾

**51-56.** ከኢብራሂም እንግዶችም (ወሬ) ንገራቸው፡፡ በእርሱ ላይ በገቡና ሰላም ባሉት ጊዜ የሆነውን አስታውስ፡፡ እርሱም፡- እኛ ከናንተ ፈሪዎች ነን አላቸው፡፡ አትፍራ እኛ ዐዋቂ በሆነ ወንድ ልጅ እናበስርሃለን አሉት፡፡ እርጅና የደረሰብኝ ከመሆኔ ጋር አበሰራችሁኝን? በምን ታበስሩኛላችሁ? አለ፡፡ በእውነት አበሰርንህ ከተስፋ ቆራጮችም አትሁን አሉ፡፡ ከጠማማዎች በስተቀር ከጌታው እዝነት ተስፋን የሚቆርጥ ማነው? አሉ፡፡

قَالَ فَمَا خَطۡبُكُمۡ أَيُّهَا ٱلۡمُرۡسَلُونَ ﴿٥٧﴾ قَالُوٓاْ إِنَّآ أُرۡسِلۡنَآ إِلَىٰ قَوۡمٖ مُّجۡرِمِينَ ﴿٥٨﴾
إِلَّآ ءَالَ لُوطٍ إِنَّا لَمُنَجُّوهُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿٥٩﴾ إِلَّا ٱمۡرَأَتَهُۥ قَدَّرۡنَآ إِنَّهَا لَمِنَ ٱلۡغَٰبِرِينَ ﴿٦٠﴾

**57-60.** እናንተ መልዕክተኞች ሆይ! እረ ለመሆኑ ነገራችሁ ምንድን ነው? አሉ። እኛ አመጸኞች ወደ ሆኑ ሕዝቦች ተልከናል አሉት። የሉጥ ቤተሰቦች ብቻ ሲቀሩ እነርሱን እኛ ሁላቸውንም በእርግጥ የምናድናቸው ነን። ሚስቱ ብቻ ስትቀር። እርሷንማ በቅጣቱ ውስጥ ከሚቀሩት ሰዎች መሆኗን ወስነናል (አሉ)።

فَلَمَّا جَآءَ ءَالَ لُوطٍ ٱلْمُرْسَلُونَ ﴿٦١﴾ قَالَ إِنَّكُمْ قَوْمٌ مُّنكَرُونَ ﴿٦٢﴾ قَالُوا۟ بَلْ جِئْنَـٰكَ بِمَا
كَانُوا۟ فِيهِ يَمْتَرُونَ ﴿٦٣﴾ وَأَتَيْنَـٰكَ بِٱلْحَقِّ وَإِنَّا لَصَـٰدِقُونَ ﴿٦٤﴾ فَأَسْرِ بِأَهْلِكَ بِقِطْعٍ مِّنَ ٱلَّيْلِ
وَٱتَّبِعْ أَدْبَـٰرَهُمْ وَلَا يَلْتَفِتْ مِنكُمْ أَحَدٌ وَٱمْضُوا۟ حَيْثُ تُؤْمَرُونَ ﴿٦٥﴾ وَقَضَيْنَآ إِلَيْهِ ذَٰلِكَ
ٱلْأَمْرَ أَنَّ دَابِرَ هَـٰٓؤُلَآءِ مَقْطُوعٌ مُّصْبِحِينَ ﴿٦٦﴾

**61-66.** መልዕክተኞቹም ሉጥንና ቤተሰቦቹን በመጡባቸው ጊዜ። ሉጥ እናንተ የተሳሳታችሁ ሕዝቦች ናችሁ አላቸው። አይደለም። እኛ ህዝቦችህ በእሱ ይጠራጠሩበት በነበሩት ቅጣት መጣንልህ አሉት። እውነትንም ይዘን መጣንልህ። እኛም በእርግጥ እውነተኞች ነን። ከቤተሰብህ ጋር በሌሊቱ ከፊል (አጋማሽ) ላይ ሒድ። በኋላቸውም ተከተል። ከናንተም አንድም ሰው ወደ ኋላው አይገላመጥ። ወደ ታዘዛችሁበትም ስፍራ እለፉ (አሉት)። ወደ እርሱም ያንን ትዕዛዝ አወረድን እርሱም የእነዚህ ሕዝቦች መጨረሻ ያነጉ ሲሆኑ (ስራቸው) መቆረጥ ነው።

وَجَآءَ أَهْلُ ٱلْمَدِينَةِ يَسْتَبْشِرُونَ ﴿٦٧﴾ قَالَ إِنَّ هَـٰٓؤُلَآءِ ضَيْفِى فَلَا تَفْضَحُونِ ﴿٦٨﴾ وَٱتَّقُوا۟
ٱللَّهَ وَلَا تُخْزُونِ ﴿٦٩﴾ قَالُوٓا۟ أَوَلَمْ نَنْهَكَ عَنِ ٱلْعَـٰلَمِينَ ﴿٧٠﴾ قَالَ هَـٰٓؤُلَآءِ بَنَاتِىٓ إِن كُنتُمْ
فَـٰعِلِينَ ﴿٧١﴾ لَعَمْرُكَ إِنَّهُمْ لَفِى سَكْرَتِهِمْ يَعْمَهُونَ ﴿٧٢﴾ فَأَخَذَتْهُمُ ٱلصَّيْحَةُ مُشْرِقِينَ ﴿٧٣﴾
فَجَعَلْنَا عَـٰلِيَهَا سَافِلَهَا وَأَمْطَرْنَا عَلَيْهِمْ حِجَارَةً مِّن سِجِّيلٍ ﴿٧٤﴾ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَـَٔايَـٰتٍ
لِّلْمُتَوَسِّمِينَ ﴿٧٥﴾ وَإِنَّهَا لَبِسَبِيلٍ مُّقِيمٍ ﴿٧٦﴾ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَـَٔايَةً لِّلْمُؤْمِنِينَ ﴿٧٧﴾

**67-77.** (የሰዶም) የከተማይቱም ሰዎች የሚያበስሩ ሆነው መጡ። ሉጥም አለ፡- እነዚህ እንግዶቼ ናቸውና አታጋልጡኝ። አላህንም ፍሩ አታሳፍሩኝም። ከዓለማት ማንንም እንዳታስተናግድ አልከለከልንህምን? አሉት። ሉጥም፡- እነዚህ ሴቶች ልጆቼ ናቸው። የምትፈፅሙ ከሆናችሁ (አግቧቸው) አለ። በዕድሜህ እንምላለን እነርሱ በእርግጥ በስካራቸው ውስጥ ይዋልላሉ። ጩኸቲቱም ፀሐይ የወጣችባቸው ሲሆኑ ያዘቻቸው። ላይዋንም ከታችዋ

አደረግን። በእነርሱም ላይ የሸክላ ድንጋዮችን አዘነብንባቸው። በዚህ ውስጥ ለተመልካቾች በእርግጥ ብዙ መገሰጫዎች አሉበት። እሷም ከተማይቱ በቀጥታ መንገድ ላይ ናት። በዚህ ውስጥ በእርግጥ ለምዕመናን መገሰጫ አለ።

وَإِن كَانَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأَيۡكَةِ لَظَٰلِمِينَ ﴿٧٨﴾ فَٱنتَقَمۡنَا مِنۡهُمۡ وَإِنَّهُمَا لَبِإِمَامٖ مُّبِينٖ ﴿٧٩﴾

**78-79.** እነሆ የአይካ* ሰዎችም በእርግጥ በዳዮች ነበሩ። ከእነርሱ ተበቀልን ሁለቱም የሉጥና የአይከት ሕዝቦች (ከተሞች) በእርግጥ በግልጽ መንገድ ላይ ናቸው።

* እነዚህ ህዝቦች የነብዩ ሹዐይብ ህዝቦች ናቸው። ይኖሩበት የነበረው አካባቢ ዛፉማ አትክልት የበዛበት ምቹ ነበር። በአላህ ሲክዱ በነብዩ ሲያምፁአትክልቷን በላያቸው ላይ አነደደባቸው። ሹዐይብ የተላኩት ለሁለት አካባቢዎች ነበር። አንደኛው ሀገር ይህ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የመድየን ሰዎች ናቸው።

وَلَقَدۡ كَذَّبَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡحِجۡرِ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿٨٠﴾ وَءَاتَيۡنَٰهُمۡ ءَايَٰتِنَا فَكَانُواْ عَنۡهَا مُعۡرِضِينَ ﴿٨١﴾
وَكَانُواْ يَنۡحِتُونَ مِنَ ٱلۡجِبَالِ بُيُوتًا ءَامِنِينَ ﴿٨٢﴾ فَأَخَذَتۡهُمُ ٱلصَّيۡحَةُ مُصۡبِحِينَ ﴿٨٣﴾
فَمَآ أَغۡنَىٰ عَنۡهُم مَّا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ﴿٨٤﴾

**80-84.** የሒጅር ሰዎች መልዕክተኞቹን በእርግጥ አስተባበሉ። ተዐምራታችንን ሰጠናቸው ከርሷም ዘንጊዎች ነበሩ። ከኮረብታዎችም ቤቶችን ፀጥተኞች ሆነው ይጠርቡ ነበር። ያነጉ ሲሆኑ ጩኸት ያዘቻቸው (ወደሙ)። ይሠሩት የነበሩት ሕንጻ ምንም አልጠቀማቸውም።

وَمَا خَلَقۡنَا ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَآ إِلَّا بِٱلۡحَقِّۗ وَإِنَّ ٱلسَّاعَةَ لَأٓتِيَةٞۖ
فَٱصۡفَحِ ٱلصَّفۡحَ ٱلۡجَمِيلَ ﴿٨٥﴾ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ ٱلۡخَلَّٰقُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٨٦﴾

**85-86.** ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በእውነት እንጂ በላግጣ አልፈጠርንም። ሰዓቲቱም በእርግጥ መጪ ናት። መልካምን ይቅርታ አድርግላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ እርሱ ያልነበረን ነገር ሁሉ ፈጣሪ፤ ዐዋቂ ነው።

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَٰكَ سَبْعًا مِّنَ ٱلْمَثَانِي وَٱلْقُرْءَانَ ٱلْعَظِيمَ ﴿٨٧﴾ لَا تَمُدَّنَّ عَيْنَيْكَ إِلَىٰ مَا مَتَّعْنَا
بِهِۦٓ أَزْوَٰجًا مِّنْهُمْ وَلَا تَحْزَنْ عَلَيْهِمْ وَٱخْفِضْ جَنَاحَكَ لِلْمُؤْمِنِينَ ﴿٨٨﴾ وَقُلْ إِنِّيٓ أَنَا ٱلنَّذِيرُ
ٱلْمُبِينُ ﴿٨٩﴾ كَمَآ أَنزَلْنَا عَلَى ٱلْمُقْتَسِمِينَ ﴿٩٠﴾ ٱلَّذِينَ جَعَلُواْ ٱلْقُرْءَانَ عِضِينَ ﴿٩١﴾ فَوَرَبِّكَ
لَنَسْـَٔلَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٩٢﴾ عَمَّا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿٩٣﴾

**87-93.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሚደጋገሙ የሆኑን ባለ ሰባት አንቀፅንና ታላቁንም ቁርኣን በሙሉ በእርግጥ ሰጠንህ። ከእነርሱ ከከሐዲያን ብዙዎችን ወገኖች በእርሱ ወደ አጣቀምንበት ፀጋ ዓይኖችህን አትዘርጋ በእነርሱም ላይ ባያምኑ አትዘን ክንፍህንም ለምዕመናን አለዝብ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ ግልጽ አስፈራሪ እኔ ነኝ በል። ሰዎችን ለማገድ የመካን በሮች በተከፋፈሉት ላይ እንደ አወረድነው በኾነ ቅጣት አስፈራሪያችሁ ነኝ (በል)። እነርሱም እነዚያ ቁርኣንን ክፍልፍሎች ያደረጉ ናቸው። በጌታህ እንምላለን ሁላቸውንም ይሠሩት ከነበሩት ነገር ሁሉ እንጠይቃቸዋለን።

فَٱصْدَعْ بِمَا تُؤْمَرُ وَأَعْرِضْ عَنِ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿٩٤﴾ إِنَّا كَفَيْنَٰكَ ٱلْمُسْتَهْزِءِينَ ﴿٩٥﴾ ٱلَّذِينَ يَجْعَلُونَ
مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَسَوْفَ يَعْلَمُونَ ﴿٩٦﴾ وَلَقَدْ نَعْلَمُ أَنَّكَ يَضِيقُ صَدْرُكَ بِمَا يَقُولُونَ ﴿٩٧﴾
فَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ وَكُن مِّنَ ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿٩٨﴾ وَٱعْبُدْ رَبَّكَ حَتَّىٰ يَأْتِيَكَ ٱلْيَقِينُ ﴿٩٩﴾

**94-99.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የታዘዝክበትንም ነገር በይፋ ግለጽ። አጋሪዎችንም ተዋቸው። ተሳላቂዎችንም ሁሉ እኛ በቅተንሃል። እነርሱም እነዚያ ከአላህ ጋር ሌላ አምላክን ያደረጉ ናቸው። በእርግጥም (ፍጻሜያቸውን) ወደፊት ያውቃሉ። አንተም በሚሉት ነገር ልብህ የሚጠብ መኾኑን እናውቃለን። ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው። ከሰጋጆቹም ሁን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እውነቱም ሞት እስኪመጣህ ድረስ ጌታህን ተገዛ።

### ከሒጂር ምዕራፍ ከአንቀፅ ከ (1-99) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ነብዩ (ﷺ) ያሳለፉት የስቃይ ሕይወት ምን ይመስል እንደነበር፤
2. አላህ ቁርኣንን ከማንኛውም የመበረዝና የመጥፋት አደጋ በሙሉ እንደሚጠብቀው ዋስትና ስለ መስጠቱ፤
3. በተለያየ ቦታና ጊዜ የነበሩ ሰዎች ነቢያት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ጎጂ ልምዳቸውን ሲያወግዙባቸው መቃወማቸውን፤

4. ከሓዲያን በግድ የአላህን ቅጣት እውን ሆኖ እስከሚያዩ ድረስ እንደማያምኑ፤
5. ከሓዲያን ተዐምራትን አሣዩን በማለት ለነቢያት ያቀረቡት ጥያቄ እንዳጠመማቸው፤
6. የመሬት አፈጣጠር የአላህን ኃያልነት የሚያሣይ ስለ መሆኑ፤
7. የመሬት ቡቃያ ማብቀል ፍጡራን ከሞት በኋላ ህያው እንደሚሆኑ የሚያስረዳ ስለ መሆኑ፤
8. ይህንን ሁሉ ተአምራት ያሳየው ብቸኛው አምላክ አላህ ስለመሆኑ፤
9. ከሞት በኋላ ሕይወት መኖሩ የማይቀር ሃቅ መሆኑን፤
10. ነብዩ (ﷺ) የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
11. የሰው ልጅ የመጀመሪያ አፈጣጠር ከጭቃ መሆኑን፤
12. ሱጁድ ታላቅ ከሆኑት የዒባዳ አይነቶች አንዱ መሆኑን፤
13. ምቀኝነት እጅግ የተወገዘ ብልሹ ሥነ ምግባር ስለመሆኑ፤
14. ኩራት የተወገዘና ለምድራዊ ሕይወትም ሆነ ለአኼራ የማይበጅ መጥፎ ባህርይ ስለመሆኑ፤
15. ጭቃ ከእሳት የበለጠና የተሻለ ነገር መሆኑን፤
16. ኢብሊስ መቸም ቢሆን የንሰሀ ዕድል የማይሰጠውና የንሰሃ በር ጭራሽ የተዘጋበት ስለመሆኑ፤
17. አላህ ለሰይጣን ጥያቄ አዎንታዊ ምላሽ እንደሰጠ ሁሉ ለከሓዲያንም አንዳንድ ጥያቂያቸው አዎንታዊ ምላሽ ሊሰጣቸው እንደሚችል፤
18. ኢብሊስ ሰዎችን ለማሳሳት ከሚጠቀምባቸው ዘዴዎች ዋነኛው ዘዴ መጥፎ ነገሮችን አስውቦ ማቅረቡ መሆኑን፤
19. ነብዩ (ﷺ) በአላህ ኃይል ከመወንጀል የተጠበቁ መሆናቸውን፤
20. ገሀነም የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት የቅጣት ስፍራ መሆኑን፤
21. የገነት ፀጋዎች ለዘለዓለም የሚቀጥሉና ማብቂያ የሌላቸው የተሟሉና ፍፁም አስደሳች ፀጋዎች መሆናቸውን፤
22. አላህ ወንጀሉን አምኖ ይቅርታ ለሚጠይቀው ባሪያው ሁሉ ይቅርታ ለመስጠት ቃል መግባቱን፤
23. እንግዳን ማስተናገድና መንከባከብ ተገቢ መሆኑን፤
24. የነብዩ ሉጥ ሰዎች በምን ምክንያት እንደጠፉና ጥፋታቸውም ግብረ ሰዶምን ይፈፅሙ ስለነበር መሆኑን፤
25. ግብረ ሰዶም እጅግ የተወገዘ የወንጀል ተግባር ስለመሆኑ፤
26. ነብዩ ሉጥ እንግዶቻቸውን ለማዳን ሲሉ በልጆቻቸው እስከ መደራደር እንደደረሱ፤
27. አላህ የነብዩን ታላቅነት ለመግለፅና ያላቸውን ክብር ለማሳየት በርሳቸው መማሉን፤
28. የአላህን ፍጡራን ሁኔታ እያስታወሱ መመራመር ተገቢ መሆኑን፤
29. የአላህ ቁጣ ኃያል መሆኑን ማስታወስ እንደሚገባ፤
30. አላህ ሊያጠፋው የፈለገውን ነገር ምንም አይነት የሳይንስና ቴክኖሎጂ የመከላከል ኃይል ሊያድነው የማይችል መሆኑን፤
31. ጭቆና በሌለበትና ነፃነት በተከበረበት አጋጣሚውን በመጠቀም ሐቅን ይፋ ማውጣት ተገቢ እንደሆነ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የአል ሂጅር ሰዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (16)
# የንብ ምዕራፍ
# (ሱረቱ አንነሕል)

سُورَةُ النَّحۡلِ

## የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (128) ናቸው።
## የሱረቱ አን-ነሕል መግቢያ

*መቶ ሃያ ስምንት አናቅፅን ይዞ በመካ የወረደ ሲሆን መግቢያው አላህ ለአጋሪዎች የዛተውን ዛቻ አጠናሮ መፈፀም እንደሚችል በመግለፅ ሰማይና ምድርን መፍጠሩ ለዚሁ ምልክት መሆኑን ያብራራል። ከዚያ በማስከተል አላህ ለሰዎች የዋለላቸውን ፀጋ ማለትም ግመልን በመፍጠር፤ ቡቃያን በማብቀል፤ በባህር ውስጥ ለሰዎች ምግብነትና ለጌጥነት የሚያገለግሉ ዓሳዎችንና ማዕድናትን መፍጠሩን አስታውሶ በእነኚህ ፀጋዎች ለጋሽ የሆነው አላህ ሊመሰገን እንደሚገባውና ለብቻው ሊመለክ እንደሚገባው ገልፆ አጋሪዎች እነኚህን ነገሮች በመመልከት ሊያምኑ ሲገባቸው በቁርአን ላይ መቅጠፋቸውና መዋሸታቸውን ያወሳል። በመቀጠልም አጋሪዎች የሚጠብቃቸውን ቅጣት አስታውሶ ለሙዕሚኖች ያዘጋጀላቸውን መልካም መስተንግዶ ያወሳል። አጋሪዎች ሙቶ መነሳትን ከመካድ አልፈው በዚሁ ጉዳይ ላይ የሚያደርጉትን ጭቅጭቅ አስታውሶ አቅማቸውን መገምገም እንዳለባቸው ይመክራል።*

*ቂያማ ርቀት እንደሌለው አላህ ሁሉን ነገር ማድረግ የሚችል መሆኑን ከሓዲያን ግን ምንም በማይችሉ ነገር ላይ ከፍተኛ ተስፋ መጣላቸው አግባብ እንዳልሆነ ይጠቁማል። የጃሂሊያ ዘመን ከሓዲያን በሴት ልጅ ላይ ህፃንም ሆና ሆነ አድጋ ይፈፅሙት የነበረው የግፍ ተግባር አስከፊ እንደነበር በመግለፅ የቀድሞ ነብያትን ታሪክ ያወሳል።*

*አላህ ከፈጠራቸው ነገሮች መካከል ልንማራቸው የሚገቡ ነገሮችን በመዘርዘር አንዱን ሀብታም ሌላውን ደሀ፤ አንዱን ወንድ ሌላዋን ሴት በማድረግ መፍጠሩን አስተምሯል። በተጨማሪ የአላህን ገደብ የለሽ ችሎታ ሲዘረዝር ከሓዲያን የአላህን ኃያልነትና ክፍተኛ ችሮታ የሚያመለክቱ ነገሮችን በአንክሮ እንዲመለከቱ ግፊት ያሳድራል። ኢስላም በፍትህ ዙሪያ ዝምድናን መቀጠልን ቃል ኪዳንን በማክበር በተመለከተ የቁርኣን ተአምርነትና ከሓዲያን በሱ መካዳቸውንና በተለይ በሱ ላይ መቅጠፋቸውን ከተናገረ በኋላ የቂያማ ቀን ከሓዲያን ምን እንደሚጠብቃቸው ያስጠነቅቃል።*

*ከሓዲያንን የሚመስሉት አይሁዶችም ቢሆኑ ሲቀጡ በጥፋታቸው ልክ መሆን እንዳለበትና ሙዕሚኖችንም መታገስና መልካም ተግባር መፈፀም እንዳለባቸው በማስተማር መልዕክቱን ያጠናቅቃል።*

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

أَتَىٰٓ أَمۡرُ ٱللَّهِ فَلَا تَسۡتَعۡجِلُوهُۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ١

**1.** (ከሓዲያን ሆይ!)፣ የአላህ ትዕዛዝ መጣ ስለዚህ አታጣድፉት። አላህ ከማይገባው ሁሉ ጠራ። ከሚያጋሩትም ሁሉ ላቀ።

ከንብ ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ በሱረቱል ኢቅተረበ መጀመሪያ ላይ ያለችው አንቀፅ በምትወርድ ጊዜ ካፊሮች እርስ በርሣቸው «ይህ ሠውዬ ቂያማ ደርሣለች እያለ ነው። ልፋታችሁን ቀነስ አድርጉ። ምን እንደሚሆን እስከናይ ድረስ» ተባብለው ምንም ሣይከሠት ሲቀር ምንም አላየንም በማለት መተቸት ጀመሩ። በዚህን ጊዜ ይህ አንቀፅ ወረደ። እነሱም በፍርሐት ሲጠባበቁ ሙሐመድ ሆይ! ያስፈራራኸን ነገር ምንም ሲከሠት አላየንም በማለታቸው ይህ አንቀፅ ወረደ ከዚያ በኋላ «እኔና ቂያማ ሁለት ጣቶቻቸውን አሣይተው እንደዚህ ሁነን ነው የተላከነው እንደውም ልትቀድመኝ ትቀርብ ነበር» በማለት የቂያማን መቃረብ በጋሃድ አስተማሩ። (ጦባሪ፤ ኢኢብኑ አልጀውዚ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يُنَزِّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ بِٱلرُّوحِ مِنۡ أَمۡرِهِۦ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦٓ
أَنۡ أَنذِرُوٓاْ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱتَّقُونِ ٢

**2.** ከባሮቹ መካከል በሚሻው ሰው ላይ መላዕክትን ከራዕይ ጋር በፈቃዱ ያወርዳል። (ከሓዲያንን በቅጣት) አስጠንቅቁ። እነሆ ከእኔ በስተቀር ሌላ አምላክ የለም። ፍሩኝም ማለትን (አስታውቁ በማለት ያወርዳል)።

خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۚ تَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٣

**3.** ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ። ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።

خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِن نُّطۡفَةٖ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٞ مُّبِينٞ ٤ وَٱلۡأَنۡعَٰمَ خَلَقَهَاۖ لَكُمۡ فِيهَا دِفۡءٞ
وَمَنَٰفِعُ وَمِنۡهَا تَأۡكُلُونَ ٥ وَلَكُمۡ فِيهَا جَمَالٌ حِينَ تُرِيحُونَ وَحِينَ تَسۡرَحُونَ ٦ وَتَحۡمِلُ
أَثۡقَالَكُمۡ إِلَىٰ بَلَدٖ لَّمۡ تَكُونُواْ بَٰلِغِيهِ إِلَّا بِشِقِّ ٱلۡأَنفُسِۚ إِنَّ رَبَّكُمۡ لَرَءُوفٞ رَّحِيمٞ ٧

**4-7.** ሰውን ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው። ከዚያ እርሱ ወዲያውኑ (ትንሣኤን በመካድ) ግልጽ ተከራካሪ ይሆናል። (ሰዎች ሆይ!) ግመልን፣ ከብትን፣ ፍየልንም፣ በእርሷ ብርድ መከላከያ ሙቀትና ሌሎች ጥቅሞችም ያሉባት

ስትሆን ለእናንተ ፈጠረላችሁ። ከእርሷም ትበላላችሁ (ትመገባላችሁ)። ለእናንተ በእርሷማ ወደ ማረፊያዋ በምትመልሷት ጊዜና ጧት ወደ ግጦሽ ቦታዋ በምታሰማሯት ወቅት ውበት አለላችሁ። ጓዞቻችሁን ነፍሶቻችሁን በማስቸገር እንጂ ወደ ማትደርሱበት አገር ትሸከማለች። ጌታችሁ በእርግጥ ሩህሩህ እና አዛኝ ነውና።*

✷ ስለ ተውሒድ ፅንሰ ሀሳብና ስለ ሙቶ መቀስቀስ እውነታነት እንማራለን።

ከንብ ምዕራፍ (4) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ኡበይ ኢብኑ ኸለፍ የሚባል ከሃዲ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ የበሠበሠ አጥንት ይዞ «ሙሐመድ ሆይ! ይህንን ነው አላህ ይቀስቅሣል የምትል» በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ -አል-ጀውዚ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَٱلۡخَيۡلَ وَٱلۡبِغَالَ وَٱلۡحَمِيرَ لِتَرۡكَبُوهَا وَزِينَةٗۚ وَيَخۡلُقُ مَا لَا تَعۡلَمُونَ ٨

8. ፈረሶችን፤ በቅሎዎችንና አህዮችን ልትጋልቧቸውና ልታጌጡባቸው ፈጠረላችሁ። የማታውቁትን ድንቅ ነገርም ወደ ፊት ይፈጥራል*።

✷ ይህ አባባል ወደ ፊት ብዙ የትራንስፖርት መጠቀሚያዎች ለሰዎች የሚያገለግሉ ነገሮች በምድርም ሆነ በባህር ዉስጥ እንደሚፈጠሩ ያመለክታል። ለዚህ አባባል እውነትነት ቁርኣን በወረደበት ዘመን እንኳንስ ሊኖሩ ቀርቶ በአዕምሮ ታስበው ያልነበሩ ብዙ ነገሮች ተፈጥረዋል። ወደ ፊትም ይፈጠራሉ። ይህም የቁርኣንን ተዐምረኛነት ከሚያመለክቱት እውነታዎች አንዱ ነው።

وَعَلَى ٱللَّهِ قَصۡدُ ٱلسَّبِيلِ وَمِنۡهَا جَآئِرٞۚ وَلَوۡ شَآءَ لَهَدَىٰكُمۡ أَجۡمَعِينَ ٩

9. በአላህ ላይ (በችሮታው) ቀጥተኛውን የመግለጽ መግለጽ ጉዳይ የአላህ ነው። ከእርሷም ጠማማ አለ። በሻም ኖሮ ሁላችሁን ባቀናችሁ ነበር።

هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗۖ لَّكُم مِّنۡهُ شَرَابٞ وَمِنۡهُ شَجَرٞ فِيهِ تُسِيمُونَ ١٠
يُنۢبِتُ لَكُم بِهِ ٱلزَّرۡعَ وَٱلزَّيۡتُونَ وَٱلنَّخِيلَ وَٱلۡأَعۡنَٰبَ وَمِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِۚ
إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ١١

10-11. እርሱ ያ ከሰማይ ውሃን ያወረደ ነው። ከእርሱ ለእናንተ መጠጥ አለላችሁ። ከእርሱም እንስሳዎችን በእርሱ ውስጥ የምታሰማሩበት ዛፍ ይበቅልበታል። በእርሱ ለእናንተ አዝመራን የዘይት ወይራን ዘምባባዎችን ወይኖችንና ከፍሬዎችም ሁሉ ያበቅልላችኋል። በዚህ ክስተት ውስጥ ለሚያስተነትኑ ሕዝቦች ሁሉ በእርግጥ ትልቅ ተዐምር አለ።

وَسَخَّرَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ وَٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ ۖ وَٱلنُّجُومُ مُسَخَّرَٰتٌۢ بِأَمْرِهِۦٓ ۗ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿١٢﴾ وَمَا ذَرَأَ لَكُمْ فِى ٱلْأَرْضِ مُخْتَلِفًا أَلْوَٰنُهُۥٓ ۗ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً لِّقَوْمٍ يَذَّكَّرُونَ ﴿١٣﴾

**12-13.** ለእናንተ ሌሊትንና ቀንን ፀሐይንና ጨረቃንም ገራላችሁ፡፡ ከዋክብትም በሙሉ በፈቃዱ ብቻ የተገሩ ናቸው፡፡ በዚህ ክስተት ውስጥ ለሚያውቁ ሕዝቦች ሁሉ በእርግጥ አያሌ ተዐምራቶች አሉ፡፡ በምድርም ላይ መልኮቹ የተለያዩ ኾኖ የፈጠረላችሁን ሁሉ ገራላችሁ፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚገሠጹ ሕዝቦች ሁሉ ግልፅ ተዐምር አለ፡፡

وَهُوَ ٱلَّذِى سَخَّرَ ٱلْبَحْرَ لِتَأْكُلُوا۟ مِنْهُ لَحْمًا طَرِيًّا وَتَسْتَخْرِجُوا۟ مِنْهُ حِلْيَةً تَلْبَسُونَهَا ۖ
وَتَرَى ٱلْفُلْكَ مَوَاخِرَ فِيهِ وَلِتَبْتَغُوا۟ مِن فَضْلِهِۦ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ﴿١٤﴾

**14.** እርሱ ያ ባሕርን ከእርሱ እርጥብ ስጋን ልትበሉና ከእርሱም የምትለብሱትን ጌጣጌጥ ታወጡ ዘንድ የገራ ነው፡፡ መርከቦችንም በውስጡ ውሃውን ቀዳጆች ኾነው ሲንሻለሉ ታያለህ፡፡ ከችሮታው ልትፈልጉና ልታመሰግኑም (ገራላችሁ)፡፡

وَأَلْقَىٰ فِى ٱلْأَرْضِ رَوَٰسِىَ أَن تَمِيدَ بِكُمْ وَأَنْهَٰرًا وَسُبُلًا لَّعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ ﴿١٥﴾
وَعَلَٰمَٰتٍ ۚ وَبِٱلنَّجْمِ هُمْ يَهْتَدُونَ ﴿١٦﴾ أَفَمَن يَخْلُقُ كَمَن لَّا يَخْلُقُ ۗ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿١٧﴾
وَإِن تَعُدُّوا۟ نِعْمَةَ ٱللَّهِ لَا تُحْصُوهَآ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَغَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٨﴾

**15-18.** በምድር ውስጥ በናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን አደረገ፡፡ ጅረቶችንና መንገዶችን ትመሩ ዘንድ (አደረገ)፡፡ ምልክቶችን (አደረገ)፡፡ በከዋክብትም እነርሱ ይመራሉ፡፡ (ሰዎች ሆይ)፣ የሚፈጥር ልክ እንደማይፈጥር ነውን? አትገሠፁምን? የአላህን ፀጋ ብትቆጥሩ አትዘልቋትም፡፡ አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና፡፡

وَٱللَّهُ يَعْلَمُ مَا تُسِرُّونَ وَمَا تُعْلِنُونَ ﴿١٩﴾ وَٱلَّذِينَ يَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَا يَخْلُقُونَ شَيْـًٔا
وَهُمْ يُخْلَقُونَ ﴿٢٠﴾ أَمْوَٰتٌ غَيْرُ أَحْيَآءٍ ۖ وَمَا يَشْعُرُونَ أَيَّانَ يُبْعَثُونَ ﴿٢١﴾ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ ۚ
فَٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْءَاخِرَةِ قُلُوبُهُم مُّنكِرَةٌ وَهُم مُّسْتَكْبِرُونَ ﴿٢٢﴾ لَا جَرَمَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ
مَا يُسِرُّونَ وَمَا يُعْلِنُونَ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ ٱلْمُسْتَكْبِرِينَ ﴿٢٣﴾

**19-23.** አላህ የምትደብቁትንና የምትገልፁትን ነገር ሁሉ ያውቃል። እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው አማልዕክት ሁሉ ምንንም አይፈጥሩም። እንዲያውም እነርሱ ራሳቸው ይፈጠራሉ። እነርሱ ሕያው ያልሆኑ ሙታን ናቸው። እራሳቸው እንኳን መቼ እንደሚቀሰቀሱ አያውቁም። (ሰዎች ሆይ)፣ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው። እነዚያም በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት ልቦቻቸው ከሓዲያን ናቸው። እነርሱም የኮሩ ናቸው አያምኑም። አላህ የሚደብቁትንና የሚገልፁትን ሁሉ የሚያውቅ ለመሆኑ ቅንጣት ያህል ጥርጣሬ የለበትም። እርሱ ኩሩዎችን አይወድም።

وَإِذَا قِيلَ لَهُم مَّاذَآ أَنزَلَ رَبُّكُمۡ قَالُوٓاْ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ٢٤ لِيَحۡمِلُوٓاْ أَوۡزَارَهُمۡ كَامِلَةٗ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ وَمِنۡ أَوۡزَارِ ٱلَّذِينَ يُضِلُّونَهُم بِغَيۡرِ عِلۡمٍۗ أَلَا سَآءَ مَا يَزِرُونَ ٢٥

**24-25.** ጌታችሁ በሙሐመድ ላይ ምን አወረደ በተባሉ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ሕዝቦች ተረቶችን ነው ይላሉ። ይህንን የሚሉት በትንሣኤ ቀን ኃጢአቶቻቸውን በሙሉና ከነዚያም ያለ ዕውቀት ሆነው ከሚያጣምሟቸው ሰዎች ኃጢአቶች ከፊሉን ሊሸከሙ ነው። ንቁ የሚሸከሙት ኃጢአት ምንኛ ከፋ፣

قَدۡ مَكَرَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ فَأَتَى ٱللَّهُ بُنۡيَٰنَهُم مِّنَ ٱلۡقَوَاعِدِ فَخَرَّ عَلَيۡهِمُ ٱلسَّقۡفُ مِن فَوۡقِهِمۡ وَأَتَىٰهُمُ ٱلۡعَذَابُ مِنۡ حَيۡثُ لَا يَشۡعُرُونَ ٢٦ ثُمَّ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يُخۡزِيهِمۡ وَيَقُولُ أَيۡنَ شُرَكَآءِيَ ٱلَّذِينَ كُنتُمۡ تُشَٰٓقُّونَ فِيهِمۡۚ قَالَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡعِلۡمَ إِنَّ ٱلۡخِزۡيَ ٱلۡيَوۡمَ وَٱلسُّوٓءَ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ ٢٧ ٱلَّذِينَ تَتَوَفَّىٰهُمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ ظَالِمِيٓ أَنفُسِهِمۡۖ فَأَلۡقَوُاْ ٱلسَّلَمَ مَا كُنَّا نَعۡمَلُ مِن سُوٓءِۭۚ بَلَىٰٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمُۢ بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ٢٨ فَٱدۡخُلُوٓاْ أَبۡوَٰبَ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ فَلَبِئۡسَ مَثۡوَى ٱلۡمُتَكَبِّرِينَ ٢٩

**26-29.** እነዚያ ከእነርሱ (ከቁረይሾች) በፊት የነበሩት ከሓዲያን በእርግጥ መከሩ። ከዚያ አላህ ሕንጻዎቻቸውን ከመሠረቶቻቸው አፈረሰ*። እናም ጣሪያው በላያቸው ላይ ወደቀባቸው። ቅጣቱም ከማያውቁት ስፍራ መጣባቸው። ከዚያ በትንሣኤ ቀን ያዋርዳቸዋል። እነዚያ በእነርሱ ጉዳይ ትከራከሩኝ የነበራችሁት ተጋሪዎቼ የት ናቸው? ይላቸዋል። እነዚያ እውቀትን የተሰጡት ክፍሎች ዛሬ ሐፍረቱና ቅጣቱ በከሓዲያን ላይ ነው ይላሉ። እነርሱ እነዚያ ነፍሶቻቸውን በዳይ ሆነው መላዕክት የሚገድሏቸው ናቸው። ከክፉ

ሥራ ምንም ነገር የምንሠራም አልነበርንም ሲሉ ታዛዥነታቸውን ይገልፃሉ። በእውነት አላህ ትሠሩት የነበራችሁትን ነገር ዐዋቂ ነው (ይባላሉ)። የገሀነምን ደጃፎች በውስጧ ዘውታሪዎች ስትኾኑ ግቡ (ይባላሉ)። የኩሩ ሰዎች መኖሪያ የሆነችው ገሀነምም በእርግጥ ከፋች!፣

✷ በዚህ አንቀፅ የተፈለገው ያ በባቢሎን ምድር ትልቅ ግንብ ገንብቶ ሲኖር ወደ ሰማይ ወጥቶ የሰማይ ፏሪዎችን ለመዋጋት አስቦ የነበረውንና አላህ በመሀል ንፋስ ልኮ በላያቸው ላይ የፈረሰባቸው የኑምሩድ ብን ከንዓን ታሪክን ነው የሚያስታውሰው። ሆኖም በዘመናችን ያሉ ከሓዲያንም የዚሁ ሰውዬ እጣ ፈንታ እንዳይገጥማቸው አስቀድመው ሊጠነቀቁ ይገባቸዋል። እንደለመዱት በውሸት ለማለፍ አስበው ወይም በእነሱ እምነትና አስተሳሰብ ጥፋት ስላልመሰላቸው።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-26) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የትንሳኤ ቀን ሩቅ መስሎ ቢታየንም ቅርብ ስለመሆኑ፤
2. ግመል፤ ፈረስ፤ አህያና ሌሎችም መሰል የጋማ ከብቶች የመፈጠራቸው ዓላማ ለግልቢያና ለትራንስፖርት አገልግሎት ስለመሆኑ፤
3. ኢስላም ተብሎ የሚታወቀው ሃይማኖት አላህና ነብዩ ያስተማሩትን የኢስላም ፅንሰ ሀሳብ የያዘው አስተምህሮት ብቻ መሆኑን፤
4. በአላህ ፍጡራን ምርምር በማድረግና በቁርኣን በማስተንተን የአላህን ኃያልነትና ፈጣሪነት መረዳት ያለውን ታላቅ ምንዳ፤
5. የአላህን ፀጋዎች በተደራራቢ ለማግኘት ጭማሪ ፀጋ ለመጎናፀፍ ዋነኛ ምክንያት አላህ ማመስገን መሆኑን፤
6. በውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳት በሙሉ አሳን ጨምሮ መብላት የተፈቀደ ስለመሆኑ፤
ሉልና መረጃን ተብለው በሚታወቁት የከበሩ ማዕዳናት ዘካ (የግዴታ ምፅዋት) የሌለ መሆኑን፤
7. ተውሒድ እጅግ ተወዳጅና ተደጋፊ ስለ መሆኑና በአንፃሩም ሽርክ የተወገዘ ስለ መሆኑ፤
8. ከሞት በኋላ ህይወት መኖሩን ያለመቀበል ለአያሌ መጥፎ ነገሮች የሚዳርግ ክህደት መሆኑን፤
9. ኩራትን አንግቦ እውነትን ያለመቀበል ከፍ ያለ ጥፋት ስለመሆኑ፤
10. ኢስላም እንዳይሰራጭ እንቅፋት የሚሆኑ ሰዎች ወንጀላቸው ትልቅ መሆኑን፤

✷ وَقِيلَ لِلَّذِينَ ٱتَّقَوْاْ مَاذَآ أَنزَلَ رَبُّكُمْۚ قَالُواْ خَيْرًاۗ لِّلَّذِينَ أَحْسَنُواْ فِي هَٰذِهِ ٱلدُّنْيَا حَسَنَةٞۚ
وَلَدَارُ ٱلْأٓخِرَةِ خَيْرٞۚ وَلَنِعْمَ دَارُ ٱلْمُتَّقِينَ ٣٠ جَنَّٰتُ عَدْنٖ يَدْخُلُونَهَا تَجْرِي مِن تَحْتِهَا
ٱلْأَنْهَٰرُۖ لَهُمْ فِيهَا مَا يَشَآءُونَۚ كَذَٰلِكَ يَجْزِي ٱللَّهُ ٱلْمُتَّقِينَ ٣١ ٱلَّذِينَ تَتَوَفَّىٰهُمُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ
طَيِّبِينَ يَقُولُونَ سَلَٰمٌ عَلَيْكُمُ ٱدْخُلُواْ ٱلْجَنَّةَ بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ٣٢

**30-32.** ለእነዚያ ለተጠነቀቁት ሰዎች ጌታችሁ ምንን ነገር አወረደ? ተባሉ። መልካምን ነገር አወረደ አሉ። ለእነዚያ ደግ ለሠሩት ህዝቦች በዚህች በቅርቢቱ ዓለም መልካም ኑሮ አለላቸው። የመጨረሻይቱም አገር በእርግጥ በላጭ ናት። የጥንቁቆቹም አገር ጀነት ምን ታምር፣ እርሷም የሚገቧትና በሥርዋ ወንዞች የሚፈሱባት ስትሆን የመኖሪያ አትክልቶች ናት። ለእነርሱም በውስጧ

የሚሹት ነገር ሁሉ አለላቸው። እንደዚሁ አላህ ጥንቁቆችን ይመነዳል። እነዚያ ጥሩ ሆነው መላዕክት ሰላም ለእናንተ ይሁን እያሉ የሚገድሏቸው ናቸው። ትሠሩት በነበራችሁት ሥራ ምክንያትም* ወደ ገነት ግቡ (ይባላሉ)።

* ጣኦታትን በአላህ ከማጋራት የፀዱ ሆነው ወይም በመልካም ተግባር ላይ ሆነው። ሙስሊም፤ አህመድ፤ ኢብኑ ማጃህ እና ሌሎች በዘገቡት ትክክለኛ ሐዲስ ነብዩ፦ «አስተካክሉ፤ አቀራርቡ ማንም ሰው በሰራው ስራ ብቻ ጀነት እንደማይገባ እወቁ» ሲሉ «እርስዎም ቢሆኑ ተብለው ሲጠየቁ «አዎ እኔም ብሆን አላህ በእዝነቱ ካላጠቃለለኝ በስተቀር» ብለዋል።

هَلۡ يَنظُرُونَ إِلَّآ أَن تَأۡتِيَهُمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ أَوۡ يَأۡتِيَ أَمۡرُ رَبِّكَۚ كَذَٰلِكَ فَعَلَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ وَمَا ظَلَمَهُمُ ٱللَّهُ وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ يَظۡلِمُونَ ﴿٣٣﴾ فَأَصَابَهُمۡ سَيِّـَٔاتُ مَا عَمِلُواْ وَحَاقَ بِهِم مَّا كَانُواْ بِهِۦ يَسۡتَهۡزِءُونَ ﴿٣٤﴾

**33-34.** (ከሓዲያን) መላዕክት ወደ እነርሱ መምጣትን ወይም የጌታህ ትዕዛዝ መምጣቱን እንጂ ይጠባበቃሉን? ከእነርሱ በፊት የነበሩት ልክ እንደዚህ ሠርተዋል። አላህ አልበደላቸውም። ግን እነርሱ ነፍሶቻቸውን የሚበድሉ ነበሩ። እናም የሠሯቸው ኃጢአቶች ቅጣት አገኛቸው። በእርሱም ይሳለቁበት የነበሩት ነገር ሁሉ በእነርሱ ላይ ወረደባቸው።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ أَشۡرَكُواْ لَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ مَا عَبَدۡنَا مِن دُونِهِۦ مِن شَيۡءٖ نَّحۡنُ وَلَآ ءَابَآؤُنَا وَلَا حَرَّمۡنَا مِن دُونِهِۦ مِن شَيۡءٖۚ كَذَٰلِكَ فَعَلَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ فَهَلۡ عَلَى ٱلرُّسُلِ إِلَّا ٱلۡبَلَٰغُ ٱلۡمُبِينُ ﴿٣٥﴾

**35.** እነዚያ (በአላህ) ጣዖታትን ያጋሩ ህዝቦች አላህ በሻ ኖሮ ከእርሱ ሌላ እኛም ሆነን አባቶቻችን ምንንም ባልተገዛን ነበር። ያለእርሱም ትዕዛዝ ምንንም እርም ባላደረግን ነበር አሉ። እነዚያም ከእነርሱ በፊት የነበሩት ህዝቦች ልክ እንደዚሁ ሠሩ። በመልዕክተኞቹም ላይ ግልጽ ማድረስ ብቻ እንጂ ሌላ የለባቸውም።

وَلَقَدۡ بَعَثۡنَا فِي كُلِّ أُمَّةٖ رَّسُولًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱجۡتَنِبُواْ ٱلطَّٰغُوتَۖ فَمِنۡهُم مَّنۡ هَدَى ٱللَّهُ وَمِنۡهُم مَّنۡ حَقَّتۡ عَلَيۡهِ ٱلضَّلَٰلَةُۚ فَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَٱنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُكَذِّبِينَ ﴿٣٦﴾

**36.** በየሕዝቡ ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣዖትን ራቁ በማለት የሚያስተምር መልዕክተኛን ልከናል። ከእነርሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለ። ከእነርሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አለ። እናም በምድር ላይ ኺዱ። የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበር ተመልከቱ።

إِن تَحۡرِصۡ عَلَىٰ هُدَىٰهُمۡ فَإِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي مَن يُضِلُّۖ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ٣٧ وَأَقۡسَمُواْ بِٱللَّهِ
جَهۡدَ أَيۡمَٰنِهِمۡ لَا يَبۡعَثُ ٱللَّهُ مَن يَمُوتُۚ بَلَىٰ وَعۡدًا عَلَيۡهِ حَقّٗا وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ
لَا يَعۡلَمُونَ ٣٨ لِيُبَيِّنَ لَهُمُ ٱلَّذِي يَخۡتَلِفُونَ فِيهِ وَلِيَعۡلَمَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَنَّهُمۡ كَانُواْ كَٰذِبِينَ ٣٩

**37-39.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመቅናታቸው* ላይ ብትጓጓ ምንም ልታደርግ አትችልም። ምክንያቱም አላህ የሚያጠመውን ሰው ማንም አያቀናውምና። ለእነርሱም ከረዳቶች ምንም የላቸውም። ጥብቅ መሐሎቻቸውን አላህ የሚሞትን ሰው አያስነሳም ሲሉ በአላህ ስም ማሉ። አባባላቸው ሐሰት ነው (ያስነሳቸዋል)። በእርሱ ላይ ቃል ኪዳን ገብቷል። አረጋግጧልም። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም። የሚቀሰቅሳቸውም ለእነርሱ ያንን በእርሱ የሚለያዩበትን ሊገልጽላቸውና እነዚያ የካዱትም እነርሱ ውሸታሞች የነበሩ መሆናቸውን እንዲያውቁ ነው።

* ‹ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «የእኔና የሕዝቦቼ ምሳሌ እሳት እየነደደ በዙሪያው ያለውን ሲያበራ እሳቱ ውስጥ እንደሚወድቁት የእሳት እራቶችና ሌሎች ነፍሳት ነው። ሰውየው ነፍሳቱን እሳቱ ውስጥ እንዳይወድቁ ይከላከላቸዋል። እነርሱ ግን እሱ ላይ ኃይለኛ ሆነው ወደ እሳቱ ይሮጣሉ» ነብዩ (ﷺ) በሓዲሱ ላይ አክለው «አሁን ምሳሌው እኔ እናንተ ወደ እሳቱ እንዳትወድቁ ስይዛችሁ ነገር ግን እናንተ እሳት ውስጥ ለመግባቱ ሙጭጭ ትላላችሁ»

ከንብ ምዕራፍ (38) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ሙስሊም በአንድ ከሃዲ ላይ ገንዘብ ነበረውና ሊቀበለው ሄዶ እየተወያዩ ሳለ ከሞት በኋላ ተስፋ የማደርገው የሚል ዐረፍተ ነገር ጣልቃ ያስገባል። ከሃዲው «ከሞት በኋላ እቀሰቀሳለሁ ትላለህ? የሞተን አላህ እንደማይቀሠቅስ በጌታዬ ምየ አረጋግጣለሁ» በማለቱ ነው። (ጠበሪ፤ ኢብኑ አል-ጀውዚ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِنَّمَا قَوۡلُنَا لِشَيۡءٍ إِذَآ أَرَدۡنَٰهُ أَن نَّقُولَ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ٤٠

**40.** ለማንኛውም ነገር መሆኑን በፈለግን ጊዜ ቃላችን ሁን ማለት ብቻ ነው። ወዲያውም ይሆናል።

وَٱلَّذِينَ هَاجَرُواْ فِي ٱللَّهِ مِنۢ بَعۡدِ مَا ظُلِمُواْ لَنُبَوِّئَنَّهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَا حَسَنَةٗۖ وَلَأَجۡرُ ٱلۡأٓخِرَةِ
أَكۡبَرُۚ لَوۡ كَانُواْ يَعۡلَمُونَ ٤١ ٱلَّذِينَ صَبَرُواْ وَعَلَىٰ رَبِّهِمۡ يَتَوَكَّلُونَ ٤٢

**41-42.** እነዚያ ከተበደሉ በኋላ በአላህ መንገድ ላይ የተሰደዱ በቅርቢቱ ዓለም መልካሚቱን አገር (መዲናን) እናሰፍራቸዋለን። የመጨረሻይቱም ዓለም ምንዳ ታላቅ ነው። ከሓዲያን ቢያውቁ ኖሮ በተከተሏቸው ነበር። እነርሱ እነዚያ የታገሡና በጌታቸውም ላይ የሚጠጉ ናቸው።

ከንብ ምዕራፍ (41) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በመካ የነበሩ የረሡል ሙሐመድ (ﷺ) ሠሀባዎች የነበረባቸውን እንግልትና ሥቃይ ተቋቁመው ወደ መዲና ሄደው ያገኙትን ምቾት ለማስታወስ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ቁርጡቢ፤ ኢብኑ -ልጀውዚ፤ ዋሒዲ፤ ኢብኑ ከሲር እና ሱዩጢ)

وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ إِلَّا رِجَالٗا نُّوحِيٓ إِلَيۡهِمۡۖ فَسۡـَٔلُوٓاْ أَهۡلَ ٱلذِّكۡرِ إِن كُنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٤٣﴾
بِٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلزُّبُرِۗ وَأَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلذِّكۡرَ لِتُبَيِّنَ لِلنَّاسِ مَا نُزِّلَ إِلَيۡهِمۡ وَلَعَلَّهُمۡ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٤٤﴾

**43-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተም በፊት ወደ እነርሱ ወሕይን (ራእይን) የምናወርድላቸውን ሰዎችን እንጂ ሌላን አልላክንም። (ሰዎች ሆይ!) የማታውቁም ከሆናችሁ የዕውቀትን ባለቤቶችን ጠይቁ። በግልጽ ማስረጃዎችና በመጽሐፍ ላክናቸው ለሰዎች ወደ እነርሱም የተወረደላቸውን ፍች ትገልጽላቸውና ያስተነትኑም ዘንድ ወደ አንተ ቁርአንን አወረድን።

ከንብ ምዕራፍ (43) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የመካ ሰወች የነብዩን (ﷺ) ነብይነት በመካድ «አላህ ሠው ከመላክ የፀዳ ነው ይልቁንስ መልአክ አይልክም ነበርን?» በማለታቸው ጊዜ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ እና ዋሒዲ)

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (27-44) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የተንኮል መጨረሻ አስከፊ ቅጣት መቀበል ስለ መሆኑ፤
2. የትንሳኤ ዕለት የሽርክ አራማጅ አጋሪዎች በሙሉ ክስረታቸውን እንደሚያወራርዱና እንደ ሚያረጋግጡ፤
3. የእውቀት ባለቤቶች ምሁራንን ታላቅነት ግልፅ መሆኑ፤
4. ግፈኞች የሞትን ፅዋ በሚቀበሉት ዕለት እጅ እንደሚሰጡና መሸነፋቸውን እንደሚያምኑ፤
5. የእምነት አራማጆች ሙዕሚኖች ሞተው ወደ ማረፊያ መቃብራቸው ሲያመሩ የጀነት ብስራት ከቀብራቸው ውስጥ እንደሚረጋግጥላቸው፤
6. በአካልና በልብ የሚከናወኑ መልካም ተግባራት ለጀነት መግቢያ ምክንያት ቢሆኑም ጀነትን ያህል ፀጋ የሚያሸልሙና የሚያሰጡ አለመሆናቸውን፤
7. አመፀኞች በምድራዊ ህይወትም ሆነ በአኼራ ቅጣት የሚጠብቃቸው ስለመሆኑ፤
8. ከሓዲያን ለጥፋታቸው የአላህን ውሳኔ እንደ ምክንያት ማቅረባቸው የማያዋጣቸው ስለመሆኑ፤
9. ወንጀሎችን ሆነ ብሎ መፈፀምና እያወቁ ኃጢአትን መዳፈር ድርብ ወንጀል መሆኑን፤
   አላህ ማንኛውንም ነገር ለመፍጠር ለማስገኘት የማይሳነው ኃያልና ችሎታ ያለው ጌታ ስለመሆኑ፤
10. ከሓዲያን ባለስልጣናትና መሪዎች ጭቆና በሚበረታና የሃይማኖትን ድንጋጌን በነፃነት ለመፈፀም በማይቻልበት ጊዜ ስደት መውጣት አስፈላጊ መሆኑን፤
11. የማያውቁትን ነገር ከአዋቂዎች ጠይቆ መረዳት ግዴታ ስለመሆኑ፤
12. ሀዲስን መረዳትና ማወቅ የኢስላምን ፅንሰ ሀሳብ ለማወቅ ሁነኛ መፍትሄ በመሆኑ አስፈላጊ የትምህርት ዘርፍ መሆኑን እንማራለን።

أَفَأَمِنَ ٱلَّذِينَ مَكَرُواْ ٱلسَّيِّـَٔاتِ أَن يَخۡسِفَ ٱللَّهُ بِهِمُ ٱلۡأَرۡضَ أَوۡ يَأۡتِيَهُمُ ٱلۡعَذَابُ مِنۡ حَيۡثُ
لَا يَشۡعُرُونَ ﴿٤٥﴾ أَوۡ يَأۡخُذَهُمۡ فِي تَقَلُّبِهِمۡ فَمَا هُم بِمُعۡجِزِينَ ﴿٤٦﴾ أَوۡ يَأۡخُذَهُمۡ عَلَىٰ تَخَوُّفٖ
فَإِنَّ رَبَّكُمۡ لَرَءُوفٞ رَّحِيمٌ ﴿٤٧﴾

**45-47.** እነዚያን መጥፎዎችን የዶለቱ ሰዎች አላህ በእነርሱ ምድርን የሚያስዉጣቸው ወይም ከማያውቁት ሥፍራ ቅጣት የሚመጣባቸው መሆኑን ተማመኑን? አይፈሩምን? ወይም ከአገር ወደ አገር በሚዘወሩበት ጊዜ በእንቅስቃሴ ላይ እያሉ የሚይዛቸው መሆኑን አይፈሩምን? እነርሱ አሸናፊዎች አይደሉም። ወይም ቀስ በቀስ በማጉደል ላይ የሚይዛቸው መኾኑን ተማመኑን? (አይፈሩምን)? ጌታችሁ ሩሕሩህ አዛኝ ነው።

أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَىٰ مَا خَلَقَ ٱللَّهُ مِن شَيۡءٖ يَتَفَيَّؤُاْ ظِلَٰلُهُۥ عَنِ ٱلۡيَمِينِ وَٱلشَّمَآئِلِ سُجَّدٗا لِّلَّهِ
وَهُمۡ دَٰخِرُونَ ﴿٤٨﴾ وَلِلَّهِ يَسۡجُدُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ مِن دَآبَّةٖ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَهُمۡ
لَا يَسۡتَكۡبِرُونَ ﴿٤٩﴾ يَخَافُونَ رَبَّهُم مِّن فَوۡقِهِمۡ وَيَفۡعَلُونَ مَا يُؤۡمَرُونَ۩ ﴿٥٠﴾

**48-50.** ወደዚያ ከማንኛውም ነገር አላህ ወደ ፈጠረው ጥላዎቹ እነርሱም የተዋረዱ ሲሆኑ ለአላህ ሰጋጆች ሆነው ከቀኝ እና ከግራዎች ወደ ሚዘወሩት አላዩምን? በሰማያትና በምድር ያለው ተንቀሳቃሽ ሁሉ መላዕክትም ለአላህ ይሰግዳሉ። እነርሱም አይኮሩም። ጌታቸውን ከበላያቸው ሲሆን ይፈሩታል። የታዘዙትን ሁሉ ይሰራሉ (ይፈጽማሉ)።

۞ وَقَالَ ٱللَّهُ لَا تَتَّخِذُوٓاْ إِلَٰهَيۡنِ ٱثۡنَيۡنِۖ إِنَّمَا هُوَ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞ فَإِيَّٰيَ فَٱرۡهَبُونِ ﴿٥١﴾
وَلَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَهُ ٱلدِّينُ وَاصِبًاۚ أَفَغَيۡرَ ٱللَّهِ تَتَّقُونَ ﴿٥٢﴾

**51-52.** አላህም አለ ሁለት አማልክት አትያዙ እርሱ አንድ አምላክ ብቻ ነው። እኔንም ብቻ ፍሩ።* በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። መገዛትም ዘወትር ሲኾን ለርሱ ብቻ ነው። ከአላህ ሌላ ያለን ትፈራላችሁን?

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከመካከላችሁ አንዱ ከአላህ ሌላ አምልኮት የሚገባው የለም። ሙሐመድም የአላህ ባሪያና መልዕክተኛ ናቸው፤ ዒሳ የአላህ ባሪያና፤ መልእክ፤ ወደ መርየም ማህፀን የነፋው «የሁን» ቃሉ መንፈስ ናቸው፤ ጀነትም በእርግጥ እውነት ነው፤ ጀሀነምም በእርግጥ እውነት ነው ብሎ የመሰከረ፤ ከዚህ በፊት የሰራቸው መልካም ስራዎች ጥቂትም ቢሆኑ እንኳ ወደ ጀነት እንዲገባ አላህ ይፈቅድለታል።»

وَمَا بِكُم مِّن نِّعۡمَةٖ فَمِنَ ٱللَّهِۖ ثُمَّ إِذَا مَسَّكُمُ ٱلضُّرُّ فَإِلَيۡهِ تَجۡـَٔرُونَ ٥٣ ثُمَّ إِذَا كَشَفَ
ٱلضُّرَّ عَنكُمۡ إِذَا فَرِيقٞ مِّنكُم بِرَبِّهِمۡ يُشۡرِكُونَ ٥٤ لِيَكۡفُرُواْ بِمَآ ءَاتَيۡنَٰهُمۡۚ فَتَمَتَّعُواْ
فَسَوۡفَ تَعۡلَمُونَ ٥٥ وَيَجۡعَلُونَ لِمَا لَا يَعۡلَمُونَ نَصِيبٗا مِّمَّا رَزَقۡنَٰهُمۡۗ
تَٱللَّهِ لَتُسۡـَٔلُنَّ عَمَّا كُنتُمۡ تَفۡتَرُونَ ٥٦

**53-56.** ማንኛውም በናንተ ላይ ያለው ፀጋ ከአላህ የተገኘ ነው ከዚያ ችግር በደረሰባችሁ ጊዜ ወደ እርሱ ብቻ ትጮሀላችሁ። ከዚያም ከናንተ ላይ ችግርን ባነሳላችሁ ጊዜ ከናንተ የሆኑ ቡድኖች ወዲያውኑ በጌታችሁ ጣዖትን ያጋራሉ። የሚያጋሩትም በሰጠናቸው ሊክዱ ነው። ተጠቀሙም ወደፊትም የሚደርስባቸውን በእርግጥ ታውቃላችሁ። ለማያውቁት ጣዖታት ከሰጠናቸው ሲሳይ ድርሻን ያደርጋሉ። በአላህ እምላለሁ ትቀጣጥፉት ከነበራችሁት ሁሉ በእርግጥ ትጠየቃላችሁ።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (45-56) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. *የአላህን ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት በቸልታ መመልከትና በራስ መተማመን ተገቢ አለ መሆኑን፤*
2. *ፍጡራን በሙሉ የአላህ ትዕዛዝን በውድ ወይም በግድ መፈፀማቸው የማይቀር ስለመሆኑ፤*
3. *ተውሒድን ዘወትር በህይወታችን ውስጥ ማንፀባረቅና የአላህን ፍራቻ በልብ ውስጥ ማሳደር ግዴታ መሆኑን፤*
4. *እምነትን ማሳደርና በሙሉ ልብ ማመን ለአንድ አላህ ብቻ እንጂ ለሌላ ለማኛውም ፍጡር እንደማይገባ፤*
5. *ፀጋዎች ይብዙም ይነሱም ሁሉም የአላህ ውለታዎች መሆናቸውን፤*
6. *ከሓዲያን የፈጠሯቸው ሰው ሰራሽ ህግጋት በሙሉ ህገ ወጥና ብልሹ የሆኑ ህግጋት በመሆናቸው በእነዚህ ህግጋት መመራትና መዳኘት እንደማይገባ እንማራለን።*

وَيَجۡعَلُونَ لِلَّهِ ٱلۡبَنَٰتِ سُبۡحَٰنَهُۥ وَلَهُم مَّا يَشۡتَهُونَ ٥٧ وَإِذَا بُشِّرَ أَحَدُهُم بِٱلۡأُنثَىٰ ظَلَّ
وَجۡهُهُۥ مُسۡوَدّٗا وَهُوَ كَظِيمٞ ٥٨ يَتَوَٰرَىٰ مِنَ ٱلۡقَوۡمِ مِن سُوٓءِ مَا بُشِّرَ بِهِۦٓۚ أَيُمۡسِكُهُۥ عَلَىٰ
هُونٍ أَمۡ يَدُسُّهُۥ فِي ٱلتُّرَابِۗ أَلَا سَآءَ مَا يَحۡكُمُونَ ٥٩

**57-59.** ለአላህም ከመላዕክት ሴቶች ልጆችን ያደርጋሉ። ጥራት ይገባው። ለእነርሱም ግን የሚፈልጉትን ወንዶች ልጆችን ያደርጋሉ። አንዳቸውም ከመሀከላቸው አንዱ በሴት ልጅ (መወለድ) በተበሰረ ጊዜ እርሱ የተቆጨ ኾኖ ፊቱ ጠቁሮ (ቅስሙ ይሰበራል)። ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት በውርደት ላይ ኾኖም ቢሆን ይያዘውን? ወይስ በአፈር ውስጥ ይደብቀውን?* በማለት ከሰዎች ይደበቃል። ንቁ፣ የሚፈርዱት ፍርድ ምንኛ ከፋ!

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አል ሙጊራህ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) ከነዚህ ነገሮች ከልክለዋል

1. አሉቧልታና ወሬን መንዛት፤
2. ሃይማኖታዊ ነክ በሆኑ ነገሮች ላይ ጥያቄዎችን ማብዛት፤
3. ገንዘብን ያለ አግባብ ማባከን፤
4. ለወላጆች ቅን አለመሆን፤
5. ሴት ልጆችን ከነሕይወታቸው መቅበር፤
6. ለሰዎች መልካም አለ መስራትን፤
7. ከሰዎች ገንዘብ መለመንን (ይከለክሉ ነበር»)

لِلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْءَاخِرَةِ مَثَلُ ٱلسَّوْءِ ۖ وَلِلَّهِ ٱلْمَثَلُ ٱلْأَعْلَىٰ ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٦٠﴾

**60.** ለእነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም ለማያምኑት ሰዎች ሁሉ መጥፎ ፀባይ አላቸው። ለአላህ ግን ታላቅ ባህሪ አለው። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

وَلَوْ يُؤَاخِذُ ٱللَّهُ ٱلنَّاسَ بِظُلْمِهِم مَّا تَرَكَ عَلَيْهَا مِن دَآبَّةٍ وَلَٰكِن يُؤَخِّرُهُمْ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى ۖ
فَإِذَا جَآءَ أَجَلُهُمْ لَا يَسْتَـْٔخِرُونَ سَاعَةً ۖ وَلَا يَسْتَقْدِمُونَ ﴿٦١﴾ وَيَجْعَلُونَ لِلَّهِ مَا يَكْرَهُونَ ۚ
وَتَصِفُ أَلْسِنَتُهُمُ ٱلْكَذِبَ أَنَّ لَهُمُ ٱلْحُسْنَىٰ ۖ لَا جَرَمَ أَنَّ لَهُمُ ٱلنَّارَ وَأَنَّهُم مُّفْرَطُونَ ﴿٦٢﴾

**61-62.** አላህ ሰዎችን በበደላቸው ሁሉ በቀጣቸው ኖሮ በምድር ላይ ከተንቀሳቃሽ ምንንም ባልተወ ነበር። ግን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል። ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት አንዲትን ሰዓት አይቆዩም። አይቀድሙም። ለአላህ የሚጠሉትን ነገር ያደርጋሉ። ለእነርሱም መልካሚቱ ሀገር አለቻቸው በማለት በምላሶቻቸው ውሸትን ይናገራሉ። ለእነርሱም እሳት ያለቻቸው መሆናቸውና እነርሱም ወደ እርሷ በቅድሚያ የሚነዱ መሆናቸው ጥርጥር የለበትም።

تَٱللَّهِ لَقَدْ أَرْسَلْنَآ إِلَىٰٓ أُمَمٍ مِّن قَبْلِكَ فَزَيَّنَ لَهُمُ ٱلشَّيْطَٰنُ أَعْمَٰلَهُمْ فَهُوَ وَلِيُّهُمُ ٱلْيَوْمَ وَلَهُمْ
عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٦٣﴾ وَمَآ أَنزَلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ إِلَّا لِتُبَيِّنَ لَهُمُ ٱلَّذِى ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِ ۙ وَهُدًى
وَرَحْمَةً لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿٦٤﴾

**63-64.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ እንምላለን ከአንተ በፊት ወደ ነበሩት ሕዝቦች በእርግጥ መልዕክተኞችን ልከናል።* ሰይጣንም ለእነርሱ ስራዎቻቸውን ሸለመላቸው። እርሱም ዛሬ ረዳታቸው ነው። ለእነርሱም ኋላ አሳማሚ ቅጣት አላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአንተ ላይ መጽሐፉን አላወረድንም። ያንን በእርሱ የተለያዩበትን ለእነርሱ ልታብራራላቸውና ለሚያምኑትም ህዝቦች መሪና እዝነት ሊሆን እንጂ።

✶ ከዚህ ታሪክ የምንማረው ብዙ ቁም ነገር ቢሆንም ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉትን እንመልከት። ቁርኣን አጥጡር (33-34)፤ አልኢስራእ፡ (88)፤ ሁድ፡ (13-14) እንዳለው ሁሉ የማይከዱ ሲሆኑ ብዙ ጊዜ ስለ እሱ ያላቸውን ግንዛቤ የተሳሳተ እየሆነ ትክክለኛውን መስመር እየለቀቀ ሄዳ። ከዚያም ስህተቱ እየተስፋፋና እየሰፋ ሄደ ከአላህ ጋር ሌላን ነገር ወደ ማጋራት ይደርሳል። ለዚህ ነው አላህ ይህን ስህተት ለማስተካከል ነብያትን በየጊዜው የላከው።

وَٱللَّهُ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَحْيَا بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَآ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ ﴿٦٥﴾
وَإِنَّ لَكُمْ فِى ٱلْأَنْعَٰمِ لَعِبْرَةً ۖ نُّسْقِيكُم مِّمَّا فِى بُطُونِهِۦ مِنۢ بَيْنِ فَرْثٍ وَدَمٍ لَّبَنًا خَالِصًا
سَآئِغًا لِّلشَّٰرِبِينَ ﴿٦٦﴾ وَمِن ثَمَرَٰتِ ٱلنَّخِيلِ وَٱلْأَعْنَٰبِ تَتَّخِذُونَ مِنْهُ سَكَرًا وَرِزْقًا حَسَنًا ۗ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿٦٧﴾ وَأَوْحَىٰ رَبُّكَ إِلَى ٱلنَّحْلِ أَنِ ٱتَّخِذِى مِنَ ٱلْجِبَالِ بُيُوتًا
وَمِنَ ٱلشَّجَرِ وَمِمَّا يَعْرِشُونَ ﴿٦٨﴾ ثُمَّ كُلِى مِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ فَٱسْلُكِى سُبُلَ رَبِّكِ ذُلُلًا ۚ يَخْرُجُ مِنۢ
بُطُونِهَا شَرَابٌ مُّخْتَلِفٌ أَلْوَٰنُهُۥ فِيهِ شِفَآءٌ لِّلنَّاسِ ۗ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَةً لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ﴿٦٩﴾

**65-69.** አላህ ከሰማይ ውሃን አወረደ። በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ህያው አደረገ። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ህዝቦች በእርግጥ ተዐምር አለ። (ሰዎች ሆይ)፤ ለእናንተ በግመል በከብት በፍየል አፈጣጠር አያሌ ምክር ሰጪ ትምህርት አለላችሁ። በሆዱ ውስጥ ካለው ከፈርስና ከደም መካከል ጥሩ ወተትን ለጠጪዎች ጣፋጭ ሲሆን እናጠጣችኋለን። ከዘንባባወችና ከወይኖችም ፍሬዎች እንመግባችኋለን ከእርሱ ጠጅንና መልካም ምግብንም ትሰራላችሁ (ታዘጋጃላችሁ)። በዚህም ውስጥ ለሚያስቡ ህዝቦች በእርግጥ ተዐምር አለ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ወደ ንብ እንዲህ ሲል (አስታወቀ) አስተማረ፡ ከተራራዎች ከዛፍና ሰዎች ከሚሠሩት ቀፎ ቤቶችን ያዢ። ከዚያም ከፍሬዎች ሁሉ ብይ የጌታሽንም መንገዶች ለአንቺ የተገሩ ሲሆኑ ግቢ። ከሆዶችዋ መልኮቹ የተለያዩ መጠጥ ይወጣል። በእርሱ ውስጥ ለሰዎች ፍቱን መድሀኒት አለበት በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ህዝቦች ተዐምር አለበት።

وَٱللَّهُ خَلَقَكُمْ ثُمَّ يَتَوَفَّىٰكُمْ ۚ وَمِنكُم مَّن يُرَدُّ إِلَىٰٓ أَرْذَلِ ٱلْعُمُرِ لِكَىْ لَا يَعْلَمَ بَعْدَ عِلْمٍ
شَيْـًٔا ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ قَدِيرٌ ﴿٧٠﴾

**70.** አላህ ፈጠራችሁ ከዚያም ይገድላችኋል። ከናንተም መካከል ከእውቀት በኋላ ምንንም ነገር እንደማያውቅ የሚሆንበት ወደ የጃጀ (በጣም ወዳረጀ) እድሜ የሚመለስ ሰው አለ። አላህ ሁሉን አዋቂ፤ ሁሉን ነገር ማድረግ የማይሳነው ቻይ ነው።

وَٱللَّهُ فَضَّلَ بَعۡضَكُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖ فِي ٱلرِّزۡقِۚ فَمَا ٱلَّذِينَ فُضِّلُواْ بِرَآدِّي رِزۡقِهِمۡ عَلَىٰ مَا مَلَكَتۡ
أَيۡمَٰنُهُمۡ فَهُمۡ فِيهِ سَوَآءٌۚ أَفَبِنِعۡمَةِ ٱللَّهِ يَجۡحَدُونَ ﴿٧١﴾

71. አላህም ከፊላችሁን በከፊሉ ላይ በሲሳይ አበለጠ። እነዚያም በላጭ የተደረጉት ሲሳያቸውን እጆቻቸው በያዟቸው ባሮች ላይ እነርሱ በእርሱ ይስተካከሉ ዘንድ መላሾች አይደሉም። ታዲያ በአላህ ፀጋ ለእርሱ ተጋሪ በማድረግ ይክዳሉን?

وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُم مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ أَزۡوَٰجٗا وَجَعَلَ لَكُم مِّنۡ أَزۡوَٰجِكُم بَنِينَ وَحَفَدَةٗ
وَرَزَقَكُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِۚ أَفَبِٱلۡبَٰطِلِ يُؤۡمِنُونَ وَبِنِعۡمَتِ ٱللَّهِ هُمۡ يَكۡفُرُونَ ﴿٧٢﴾

72. አላህ ከነፍሶቻችሁ (ከጎሳዎቻችሁ) ለእናንተ ሚስቶችን አደረገ (የትዳር አጋሮችን ፈጠረ) ለእናንተም ከሚስቶቻችሁ ወንዶች ልጆችን የልጅ ልጆችንም አደረገላችሁ። ከመልካሞችም ፀጋዎች ሰጣችሁ። ታዲያ በውሸት (በጣኦት) ያምናሉን? በአላህ ፀጋ ይክዳሉን?

وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَمۡلِكُ لَهُمۡ رِزۡقٗا مِّنَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ شَيۡـٔٗا
وَلَا يَسۡتَطِيعُونَ ﴿٧٣﴾ فَلَا تَضۡرِبُواْ لِلَّهِ ٱلۡأَمۡثَالَۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ وَأَنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٧٤﴾

73-74. ከአላህ ሌላ ከሰማያትና ከምድር ምንንም ሲሳይ የማይሰጧቸውንና ምንንም የማይችሉትን ያመልካሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለአላህ አምሳያዎችን አታድርጉ። አላህ መሳይ እንደሌለው ያውቃል።* እናንተ ግን አታውቁም።

* ይህ ጉዳይ በቁርአን ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው ስለመሆኑ በአጭሩ ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ጉዳዮች ማየት ያስፈልጋል። «እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም ....» (አንነህል፡ 74)
«ሰማያትና ምድርን ፈጣሪ ነው። ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ...» (አሽሹራ፡ 11)
«እርሱ በሰማያትና በምድር እንዲሁም በሁለቱም ....» (መርየም፡ 65)
«ለእርሱ አንድም ብጤ የለውም» አል. ኢኽላስ እንዳለው ስለመሆኑ እንማራለን።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (57-74) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የመካ መሀይማን ሙሽሪኮች ሴትን ልጅ ይጠሉና ይፀየፏት እንደነበር፤
2. ሰዎች በጃሂሊያ ስርዓት ጊዜ አላህን በተመለከተ የነበራቸው ግንዛቤ በድንቁርናና በመሀይምነት የተከበበ እንደነ በር፤
3. ሙቶ መነሳት መኖሩን የማያምኑ ከሓዲያን ያላቸው እምነት የተበላሸ መሆኑን፤
4. አላህ በፈለገው ነገር ሁሉ የመማል መብትና ችሎታ ያለው መሆኑን በአንፃሩ ግን ሰው መማል የሚችለው በአላህ ብቻ ስለመሆኑ፤

5. አላህ ከዚህ ዑመት በፊት ለነበሩ ቀደምት ህዝቦችም አስተማሪ መልዕክተኛ ልኮላቸው የነበረ ቢሆንም ብዙዎቹ የመልዕክተኛውን ጥሪ እንዳይሰሙ ሰይጣን አሳስቷቸው የነበረ መሆኑንና በዚህም ምክንያት የአላህ ቁጣ እንዳጠፋቸው፤
6. የአላህ መልዕክተኛ ተልዕኮ ምን እንደነበረና ተልዕኳቸውን በትዕግስት ሊወጡ እንደሚገባ የሚያፅናና ቁርአናዊ አንቀፅ፤
7. ቁርኣን ለሰዎች እዝነትና ብርሃን እንዲሁም ቀና መንገድና ትክክለኛውን ጎዳና አመላካች መፅሀፍ ስለመሆኑ፤
8. ከሞት በኋላ መነሳት ሁለተኛውን ህይወት ለመጀመር የሚያስችል የመጨረሻ ዓለም ህይወት የመጀመሪያው መጀመሪያ ስለመሆኑ፤
9. የአላህ ፀጋ ከፍተኛና ዘወትር ከህሊናችን ሊጠፋ የማይገባ ስለመሆኑ፤
10. የአላህን ችሎታ የሚያሳዩ ነገሮችን ማውሳት የሚገባ መሆኑን፤
11. የአዕምሮ ታላቅነትንና በአዕምሮ ተጠቅሞ ማሰብ ምን ያህል ተፈላጊ ጉዳይ ስለመሆኑ፤
12. አላህ ዓለምን ጠቅላላ ማለት ሰዎችን ሰማይ ምድርን በሙሉ በማስተናበርና ማስተዳደር ብቸኛ ስለ መሆኑ፤
13. ከአላህ ቅጣት መተማመን ተገቢ እንዳሆነና ረጅምና ሰፊ እቅድ እያወጡ በዱንያ መታለል ተገቢ እንዳልሆነ፤
14. ከአላህ ተዐምሮች መዘናጋት እንደማይገባና ሁልጊዜ የአላህን ተዐምራት መከታተልና ማምሰልሰል እንደሚገባ፤
15. በየትኛውም ጉዳይ ላይ አባካኝነት የተወገዘ መሆኑን፤
16. የአላህን ትዕዛዝ ከመቃረን መጠንቀቅ እንዳለብን፤
17. የአላህ ፈተናዎች ሲመጡብን በትዕግስት ማለፍ እንዳለብን፤
18. ሰዎች ላይ በደረሰውና እየደረሰ ባለው ቅጣት መገሰፅና እነሱን ካጠፋው ስህተት መራቅ፤
19. ፀጥታና ሰላም የልማት፤ የፍቅርና የደህንነት ዋልታ መሆኑን፤
20. አላህን መፍራት ሁልጊዜም የሪዝቅ በር መክፈቻ መሆኑን፤
21. የዱዓ አስፈላጊነትን፤
22. የሸርክን ተግባራት በሙሉ ከህብረተሰቡ መንግሎ ማውጣት የሚያስፈልግ መሆኑን፤
23. የከሓዲያን ተግባር እጅግ የከፋ ድርጊት ስለመሆኑ፤
24. ያለምንም እውቀት ለአላህ የማይገቡ ምሳሌዎችን የሚጠቅሱ ሰዎች ተግባር የተወገዘ ስለ መሆኑ እንማራለን።

۞ ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا عَبۡدًا مَّمۡلُوكًا لَّا يَقۡدِرُ عَلَىٰ شَيۡءٖ وَمَن رَّزَقۡنَٰهُ مِنَّا رِزۡقًا حَسَنًا فَهُوَ يُنفِقُ مِنۡهُ سِرًّا وَجَهۡرًاۖ هَلۡ يَسۡتَوُۥنَۚ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِۚ بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٧٥﴾

75. በምንም ላይ የማይችለውንና በይዞታ ያለውን ባሪያና (አገልጋይና) ከእኛ መልካም ሲሳይን የሰጠነውንና እርሱም ከእርሱ ከሰጠነው በሚስጥርና በግልጽ የሚለግሰውን ነፃ ሰው አላህ ለጣኦትና ለእርሱ ምሳሌ አደረገ። (ሁለቱ) ይስተካከላሉን? በፍጹም አይስተካከሉም ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይሁን። በእውነቱ አብዛኞቻቸው አያውቁም።

ከንብ ምዕራፍ ከ (75-76) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- አንድ የመካ ሰው ባሪያውን ዲን እንዳይዝ ሰደቃ እንዳይሰጥ ይከለክለው ስለነበር ነው።

وَضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا رَّجُلَيۡنِ أَحَدُهُمَآ أَبۡكَمُ لَا يَقۡدِرُ عَلَىٰ شَيۡءٖ وَهُوَ كَلٌّ عَلَىٰ مَوۡلَىٰهُ أَيۡنَمَا يُوَجِّههُّ لَا يَأۡتِ بِخَيۡرٍ هَلۡ يَسۡتَوِي هُوَ وَمَن يَأۡمُرُ بِٱلۡعَدۡلِ وَهُوَ عَلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٧٦

76. አላህ ሁለትን ወንዶች (ለከሓዲያን ለምዕመናን) ምሳሌ አደረገ አንደኛቸው በምንም ነገር ላይ የማይችል ዲዳ ነው። እርሱም በጌታው ላይ ሸክም ነው ወደ የትም ቢያዞረው ደግ ነገር አያመጣም እርሱና ያ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ሆኖ በማስተካከል (ፍትህ) የሚያዘው ሰው ይስተካከላሉን?

وَلِلَّهِ غَيۡبُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَآ أَمۡرُ ٱلسَّاعَةِ إِلَّا كَلَمۡحِ ٱلۡبَصَرِ أَوۡ هُوَ أَقۡرَبُۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٧٧

77. በሰማያትና በምድር ያለው ሩቅ ምስጢር የአላህ ነው። የሰዓቲቱም ነገር መምጣቷ እንደ ዓይን ቅጽበት እንጂ አይደለም። ወይም እርሱ ይበልጥ የቀረበ ነው። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

وَٱللَّهُ أَخۡرَجَكُم مِّنۢ بُطُونِ أُمَّهَٰتِكُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ شَيۡـٔٗا وَجَعَلَ لَكُمُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَٱلۡأَفۡـِٔدَةَ لَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ٧٨

78. አላህ ከእናቶቻችሁ ሆዶች ምንም የማታውቁ ሆናችሁ አወጣችሁ። ታመሰግኑ ዘንድም ለእናንተ መስሚያንና ማያዎችን ልቦችንም አደረገላችሁ (ፈጠረላችሁ)።

أَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَى ٱلطَّيۡرِ مُسَخَّرَٰتٖ فِي جَوِّ ٱلسَّمَآءِ مَا يُمۡسِكُهُنَّ إِلَّا ٱللَّهُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ٧٩

79. ወደ በራሪዎችም በሰማይ አየር ውስጥ ለመብረር የተገሩ ሲሆኑ ከመውደቅ አላህ እንጂ ሌላ የማይዛቸው ሆነው አይመለከቱምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ህዝቦች ሁሉ በእርግጥ አያሌ ተዐምራቶች አሉ።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (57-79) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ምሳሌዎችን ለትምህርት መስጫነት መጠቀምና ማቅረብ ተፈላጊ ስለመሆኑ፤
2. የከሃዲና የሙስሊም ልዩነት በምሳሌ ሲቀመጥ ከሃዲ መንፈሱ እንደሞተና ሙስሊም ግን ህያው የሆነ መንፈስ እንዳለው ተደርገው የሚመሰሉ መሆኑን እንማራለን።

وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُم مِّنۢ بُيُوتِكُمۡ سَكَنٗا وَجَعَلَ لَكُم مِّن جُلُودِ ٱلۡأَنۡعَٰمِ بُيُوتٗا تَسۡتَخِفُّونَهَا
يَوۡمَ ظَعۡنِكُمۡ وَيَوۡمَ إِقَامَتِكُمۡ وَمِنۡ أَصۡوَافِهَا وَأَوۡبَارِهَا وَأَشۡعَارِهَآ أَثَٰثٗا وَمَتَٰعًا إِلَىٰ
حِينٖ ٨٠ وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُم مِّمَّا خَلَقَ ظِلَٰلٗا وَجَعَلَ لَكُم مِّنَ ٱلۡجِبَالِ أَكۡنَٰنٗا وَجَعَلَ
لَكُمۡ سَرَٰبِيلَ تَقِيكُمُ ٱلۡحَرَّ وَسَرَٰبِيلَ تَقِيكُم بَأۡسَكُمۡۚ كَذَٰلِكَ يُتِمُّ نِعۡمَتَهُۥ عَلَيۡكُمۡ
لَعَلَّكُمۡ تُسۡلِمُونَ ٨١

**80-81.** አላህም ከቤቶቻችሁ ለእናንተ መርጊያን (ማረፊያን) አደረገላችሁ (ፈጠረላችሁ)፡፡ ከእንስሳዎችም ቆዳዎች በጉዟችሁ ቀንም ሆነ በመቀመጫችሁ ቀን የምታቀሏቸውን ቤቶች ለእናንተ ፈጠረላችሁ፡፡ ከበግዋ ሱፎች ከግመልዋም ጸጉሮች ከፍየልዋም ጸጉሮች የቤት እቃዎችን እስከ ጊዜም ድረስ መጠቃቀሚያን (አደረገላችሁ)፡፡ አላህ ከፈጠረው ነገር ለእናንተ ጥላዎችን ፈጠረላችሁ፡፡ ከጋራዎችም መከለያዎችን ፈጠረላችሁ፡፡ ሐሩርንም (ወይም ብርድን) የሚጠብቋችሁን ልብሶች፤ የጦራችሁንም አደጋ የሚጠብቋችሁን ጥሩሮች ፈጠረላችሁ፡፡ እንደዚሁ ትሰልሙ ዘንድ ፀጋውን በእናንተ ላይ ይሞላል፡፡

فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَإِنَّمَا عَلَيۡكَ ٱلۡبَلَٰغُ ٱلۡمُبِينُ ٨٢ يَعۡرِفُونَ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ ثُمَّ يُنكِرُونَهَا
وَأَكۡثَرُهُمُ ٱلۡكَٰفِرُونَ ٨٣

**82-83.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከኢስላም ቢሸሹ በአንተ ላይ ያለብህ ግልጽ ማድረስ ብቻ ነው፡፡ የአላህን ፀጋ ያውቃሉ፡፡ ሆኖም ከዚያ ይክዷታል፡፡ አብዛኞቻቸውም ከሓዲያን ናቸው፡፡

وَيَوۡمَ نَبۡعَثُ مِن كُلِّ أُمَّةٖ شَهِيدٗا ثُمَّ لَا يُؤۡذَنُ لِلَّذِينَ كَفَرُواْ وَلَا هُمۡ يُسۡتَعۡتَبُونَ ٨٤ وَإِذَا
رَءَا ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ ٱلۡعَذَابَ فَلَا يُخَفَّفُ عَنۡهُمۡ وَلَا هُمۡ يُنظَرُونَ ٨٥ وَإِذَا رَءَا ٱلَّذِينَ أَشۡرَكُواْ
شُرَكَآءَهُمۡ قَالُواْ رَبَّنَا هَٰٓؤُلَآءِ شُرَكَآؤُنَا ٱلَّذِينَ كُنَّا نَدۡعُواْ مِن دُونِكَۖ فَأَلۡقَوۡاْ إِلَيۡهِمُ ٱلۡقَوۡلَ إِنَّكُمۡ
لَكَٰذِبُونَ ٨٦ وَأَلۡقَوۡاْ إِلَى ٱللَّهِ يَوۡمَئِذٍ ٱلسَّلَمَۖ وَضَلَّ عَنۡهُم مَّا كَانُواْ يَفۡتَرُونَ ٨٧ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ
وَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ زِدۡنَٰهُمۡ عَذَابٗا فَوۡقَ ٱلۡعَذَابِ بِمَا كَانُواْ يُفۡسِدُونَ ٨٨

**84-88.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከየህዝቡ ሁሉ መስካሪን የምንቀሰቅስበትን ቀን (አስታውስ)። ከዚያ ለእነዚያ ለካዱት ንግግር አይፈቀድላቸውም። እነርሱም በወቀሳ አይታለፉም። እነዚያ የበደሉ ሰዎች ቅጣትን ባዩ ጊዜ ለእነርሱ አይቃለልላቸውም። እነሱም ጊዜም አይሰጣቸውም። እነዚያ በአላህ ያጋሩት ሰዎች ተጋሪዎቻቸውን ባዩ ጊዜ ጌታችን ሆይ፣ እነዚህ ከአንተ ሌላ እናመልካቸው የነበሩ ተጋሪዎቻችን ናቸው ይላሉ። አማልክቶችም በእርግጥ እናንተ ውሸታሞች ናችሁ በማለት ቃሉን ወደ እነርሱ መልሰው ይወረውራሉ። አጋሪዎቹ በዚያ ቀንም ታዛዥነታቸውን ወደ አላህ ያቀርባሉ። ይቀጣጥፉት የነበሩትም ሁሉ ከእነርሱ ይጠፋባቸዋል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱና ከአላህ መንገድ የከለከሉ ያጠፋ በነበሩት ምክንያት ቅጣትን በቅጣት ላይ ጨመርንባቸው።

وَيَوْمَ نَبْعَثُ فِى كُلِّ أُمَّةٍ شَهِيدًا عَلَيْهِم مِّنْ أَنفُسِهِمْ ۖ وَجِئْنَا بِكَ شَهِيدًا عَلَىٰ هَٰٓؤُلَآءِ ۚ وَنَزَّلْنَا
عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ تِبْيَٰنًا لِّكُلِّ شَىْءٍ وَهُدًى وَرَحْمَةً وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ ﴿٨٩﴾

**89.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በየህዝቡ ሁሉ ውስጥ ከጎሳቸው በራሳቸው ላይ መስካሪን የምንቀሰቅስበትንና አንተንም በእነዚህ ሕዝቦች ላይ መስካሪ አድርገን የምናመጣብህን ቀን (አስታውስ)። መጽሐፉንም ለሁሉም ነገር አብራሪ፣ መመሪያ፣ እዝነትና ለሙስሊሞች አብሳሪ ሆኖ በአንተ ላይ አወረድነው።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (80-89) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ጣኦታት የቂያማ ዕለት አምላኪዎቻቸውን ያደረጉላቸው የነበሩትን የአምልኮ ተግባራት በሙሉ እነርሱ ያላዘዟቸው መሆኑን በመናዘዝ ራሳቸውን ከድርጊቱ ነፃ እንደሚያወጡ፤
2. ሰዎችን ወደ ሽርክ ጎዳና የሚገፉ ሰዎች የሚቀምሱት ቅጣት ከብደቱ ምንያህል የጠነከረ እንደሆነ፤
3. የቁርአንን መልዕክት ግልፅ ሆኖ ከወረደ በኋላ ሰዎች ኢስላምን አልሰማሁም በማለት የሚያቀርቡት ምክንያት ተቀባይነት እንደማያገኝ እንማራለን።

۞إِنَّ ٱللَّهَ يَأْمُرُ بِٱلْعَدْلِ وَٱلْإِحْسَٰنِ وَإِيتَآئِ ذِى ٱلْقُرْبَىٰ وَيَنْهَىٰ عَنِ ٱلْفَحْشَآءِ وَٱلْمُنكَرِ
وَٱلْبَغْىِ ۚ يَعِظُكُمْ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ ﴿٩٠﴾ وَأَوْفُوا۟ بِعَهْدِ ٱللَّهِ إِذَا عَٰهَدتُّمْ وَلَا تَنقُضُوا۟ ٱلْأَيْمَٰنَ
بَعْدَ تَوْكِيدِهَا وَقَدْ جَعَلْتُمُ ٱللَّهَ عَلَيْكُمْ كَفِيلًا ۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ مَا تَفْعَلُونَ ﴿٩١﴾

**90-91.** አላህ በማስተካከል (በፍትህ)፣ በማሳመር (በመልካም ሥራ) እና ለዘመድ በመስጠት ያዛል፤ ከአስከፊ (ፀያፍ ነገር)፣ ከማመንዘር፣ ከሚጠላ ነገር

ሁሉ ከመበደልም ይከለክላል። ትገነዘቡ ዘንድ ይገሥጻችኋል። (ሙስሊሞች ሆይ!) ቃል ኪዳን በገባችሁ ጊዜ በአላህ ቃል ኪዳን ሙሉ። መሓሎቻችሁንም ከአጠነከራችኋት በኋላና አላህን በእናንተ ላይ መስካሪ ያደረጋችሁ ስትኾኑ አታፍርሱ። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ያውቃልና።

وَلَا تَكُونُواْ كَٱلَّتِي نَقَضَتۡ غَزۡلَهَا مِنۢ بَعۡدِ قُوَّةٍ أَنكَٰثٗا تَتَّخِذُونَ أَيۡمَٰنَكُمۡ دَخَلَۢا بَيۡنَكُمۡ أَن تَكُونَ أُمَّةٌ هِيَ أَرۡبَىٰ مِنۡ أُمَّةٍۚ إِنَّمَا يَبۡلُوكُمُ ٱللَّهُ بِهِۦۚ وَلَيُبَيِّنَنَّ لَكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ مَا كُنتُمۡ فِيهِ تَخۡتَلِفُونَ ﴿٩٢﴾

92. ቃል ኪዳናችሁን በማፍረስ አንዲቱ ሕዝብ እርሷ ከሌላይቱ ሕዝብ የበዛች ለመኾንዋ በመካከላችሁ መሓሎቻችሁን ለክዳት መግቢያ አድርጋችሁ የምትይዙ ስትኾኑ እንደዚያች ፈትልዋን ከጠነከረ በኋላ ትርትሮች አድርጋ እንዳፈረሰችው ሴት አትኹኑ። አላህ በእርሱ ይሞክራችኋል በትንሣኤ ቀንም በእርሱ ትለያዩበት የነበራችሁትን ነገር በእርግጥ ያብራራላችኋል።

وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَجَعَلَكُمۡ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ وَلَٰكِن يُضِلُّ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِي مَن يَشَآءُۚ وَلَتُسۡـَٔلُنَّ عَمَّا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٩٣﴾

93. አላህ በፈለገ ኖሮ አንዲት ሕዝብ ባደረጋችሁ ነበር። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያጠማል። የሚሻውን ሰው ያቀናል። ትሠሩት ከነበራችሁት ሁሉ በእርግጥ ትጠየቃላችሁ።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (90-93) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ፍትህን ማስፈን፣ ዘመድን መርዳት፣ ዝምድናን መቀበል ከመልካም ስራዎች የሚቆጠሩና በሙስሊሞች ላይ ግዴታ የተደረጉ ተግባራት ስለ መሆናቸው፣
2. ዝሙት፣ ግብረ ሰዶም እንዲሁም ሌሎች አስቀያሚ ተግባራት የተከለከሉ ስለመሆናቸው፣
3. በተለያየ መልኩ የሚፈፀሙ የግፍ ተግባራት በፍፁም የተከለከሉ ስለመሆናቸው፣
4. ቃልን ማክበር ኢስላማዊ ግዴታ ስለመሆኑ፣
5. መሀላ ማፍረስ የተከለከለ መሆኑን እንማራለን።

وَلَا تَتَّخِذُوٓاْ أَيۡمَٰنَكُمۡ دَخَلَۢا بَيۡنَكُمۡ فَتَزِلَّ قَدَمُۢ بَعۡدَ ثُبُوتِهَا وَتَذُوقُواْ ٱلسُّوٓءَ بِمَا صَدَدتُّمۡ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَلَكُمۡ عَذَابٌ عَظِيمٞ ﴿٩٤﴾

**94.** ጫማዎች ከተደላደሉ በኋላ እንዳያንዳልጡ ከአላህ መንገድ በመከልከላችሁ ምክንያት ቅጣትን እንዳትቀምሱ መሓሎቻችሁን በመካከላችሁ ለክዳት መግቢያ አድርጋችሁ አትያዙ ለእናንተም ያን ጊዜ ታላቅ ቅጣት አለባችሁ።

وَلَا تَشْتَرُواْ بِعَهْدِ ٱللَّهِ ثَمَنًا قَلِيلًاۚ إِنَّمَا عِندَ ٱللَّهِ هُوَ خَيْرٌ لَّكُمْ إِن كُنتُمْ تَعْلَمُونَ ﴿٩٥﴾
مَا عِندَكُمْ يَنفَدُ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ بَاقٍۗ وَلَنَجْزِيَنَّ ٱلَّذِينَ صَبَرُوٓاْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ
يَعْمَلُونَ ﴿٩٦﴾ مَنْ عَمِلَ صَٰلِحًا مِّن ذَكَرٍ أَوْ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَنُحْيِيَنَّهُۥ حَيَوٰةً طَيِّبَةًۖ
وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَجْرَهُم بِأَحْسَنِ مَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿٩٧﴾

**95-97.** በአላህ ቃል ኪዳን ጥቂትን ዋጋ አትግዙ የምታውቁ ብትኾኑ አላህ ዘንድ ያለው ምንዳ ለእናንተ በላጭ ነውና። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እናንተ ዘንድ ያለው ሁሉ ያልቃል። አላህ ዘንድ ያለው ግን ለዘለዓለም ቀሪ ነው (አያልቅም)። እነዚያን የታገሡትን ይሠሩት በነበሩት መልካሙ ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን። ከወንድም ይሁን ከሴት እርሱ አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን። ይሠሩት ከነበሩት ነገር በመልካሙም ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን።

فَإِذَا قَرَأْتَ ٱلْقُرْءَانَ فَٱسْتَعِذْ بِٱللَّهِ مِنَ ٱلشَّيْطَٰنِ ٱلرَّجِيمِ ﴿٩٨﴾ إِنَّهُۥ لَيْسَ لَهُۥ سُلْطَٰنٌ
عَلَى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ﴿٩٩﴾ إِنَّمَا سُلْطَٰنُهُۥ عَلَى ٱلَّذِينَ يَتَوَلَّوْنَهُۥ
وَٱلَّذِينَ هُم بِهِۦ مُشْرِكُونَ ﴿١٠٠﴾

**98-100.** ቁርኣንን ለማንበብ ባሰብክ ጊዜ እርጉም ከኾነው ሰይጣን በአላህ ተጠበቅ። እርሱ በእነዚያ በትክክል ባመኑትና በጌታቸው ላይ በሚጠጉት ላይ ለእርሱ ሥልጣን የለውምና። ሥልጣኑ በእነዚያ በሚታዘዙት ላይና በእነዚያም እነርሱ በእርሱ (ምክንያት) አጋሪዎች በኾኑት ላይ ብቻ ነው።

وَإِذَا بَدَّلْنَآ ءَايَةً مَّكَانَ ءَايَةٍ وَٱللَّهُ أَعْلَمُ بِمَا يُنَزِّلُ قَالُوٓاْ إِنَّمَآ أَنتَ مُفْتَرٍۭۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ
لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٠١﴾ قُلْ نَزَّلَهُۥ رُوحُ ٱلْقُدُسِ مِن رَّبِّكَ بِٱلْحَقِّ لِيُثَبِّتَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَهُدًى
وَبُشْرَىٰ لِلْمُسْلِمِينَ ﴿١٠٢﴾

**101-102.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአንቀጽ ስፍራ አንቀጽን በለወጥን ጊዜ አላህ የሚያወርደውን ነገር ዐዋቂ ነው። አንተ ቀጣፊ እንጂ ሌላ አይደለህም ይላሉ። በእውነቱ አብዛሀኞቻቸው አያውቁም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ያመኑትን ሰዎች ለማረጋጋት ሙስሊሞቹንም ለመምራትና ለማብሰር ቁርኣንን ጂብሪል እውነተኛ ሲኾን ከጌታህ አወረደው በላቸው።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (94-102) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቁርኣን ንባብ ሲጀመር አኡዙ ቢላሂ ሚነ ሸይጧን ረጂም ብሎ መጀመሩ ተወዳጅ ስለ መሆኑ፤
2. በአላህ ላይ የሚመካ አማኝ በፍፁም የሰይጣን ተንኮል ሴራ የማያሰጋው መሆኑንና የሰይጣን ኃይል የማጥመም ተንኮሉ የሚሰራው በሙሽሪኮች ላይ ስለ መሆኑ፤
3. የቁርኣንን ህግጋት በተመለከተ የሚሻሩ ህግጋትን ምክንያት ዝርዝር እንማራለን።

وَلَقَدْ نَعْلَمُ أَنَّهُمْ يَقُولُونَ إِنَّمَا يُعَلِّمُهُۥ بَشَرٌ ۗ لِّسَانُ ٱلَّذِى يُلْحِدُونَ إِلَيْهِ أَعْجَمِىٌّ وَهَٰذَا
لِسَانٌ عَرَبِىٌّ مُّبِينٌ ﴿١٠٣﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ لَا يَهْدِيهِمُ ٱللَّهُ وَلَهُمْ عَذَابٌ
أَلِيمٌ ﴿١٠٤﴾ إِنَّمَا يَفْتَرِى ٱلْكَذِبَ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ ۖ وَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْكَٰذِبُونَ ﴿١٠٥﴾

**103-105.** እነርሱም እርሱን ቁርኣንን የሚያስተምረው ሰው ብቻ ነው ማለታቸውን በእርግጥ እናውቃለን የዚያ ወደ እርሱ የሚያስጠጉበት ሰው ቋንቋ (ዐረበኛ ያልሆነ) ዐጀምኛ ነው። ይህ (ቁርኣን) ግን በግልጽ በዐረብኛ ቋንቋ የተነገረ ነው። እነዚያን በአላህ አንቀፆች የማያምኑትን አላህ አይመራቸውም። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። ውሸትን የሚቀጣጥፉት እነዚያ በአላህ አንቀፆች የማያምኑት ብቻ ናቸው። እነዚያም ውሸታሞቹ እነሱ ብቻ ናቸው።

ከንብ ምዕራፍ (103) ኛ አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) አይን ተምዐ ከሚባል ቦታ ከመጡ ሁለት የክርስትና እምነት ተከታዮች «በቋንቋቸው የራሳቸውን መፅሐፍ ያነቡ ከነበሩ ሰዎች ነው የተማረው» ይሉ በነበሩት በመካ ሰዎች ንግግር ምክንያት ነው የወረደው። ነብዩ (ﷺ) በአጠገባቸው እያለፉ ያነቡት የነበረውን ያዳምጧቸው ነበር። አላህ እኒህ ነብዩን አስተማሩ የሚሏቸው ሰዎች ቋንቋ አረብኛ አይደለም። የሙሐመድ ቋንቋ ደግሞ አረብኛ ነው። እንዴት ይገናኝላቸኋል በማለት አባባሉ ውሸት መሆኑን አረጋገጠ።

مَن كَفَرَ بِٱللَّهِ مِنۢ بَعْدِ إِيمَٰنِهِۦٓ إِلَّا مَنْ أُكْرِهَ وَقَلْبُهُۥ مُطْمَئِنٌّۢ بِٱلْإِيمَٰنِ وَلَٰكِن مَّن
شَرَحَ بِٱلْكُفْرِ صَدْرًا فَعَلَيْهِمْ غَضَبٌ مِّنَ ٱللَّهِ وَلَهُمْ عَذَابٌ عَظِيمٌ ﴿١٠٦﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمُ
ٱسْتَحَبُّوا۟ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا عَلَى ٱلْءَاخِرَةِ وَأَنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿١٠٧﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ
ٱلَّذِينَ طَبَعَ ٱللَّهُ عَلَىٰ قُلُوبِهِمْ وَسَمْعِهِمْ وَأَبْصَٰرِهِمْ ۖ وَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْغَٰفِلُونَ ﴿١٠٨﴾ لَا جَرَمَ أَنَّهُمْ
فِى ٱلْءَاخِرَةِ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿١٠٩﴾

**106-109.** ከእምነቱ በኋላ በአላህ የካደ ሰው ብርቱ ቅጣት አለው ልቡ በእምነት የረካ ኾኖ በክሕደት ቃል በመናገር የተገደደ ሰው ብቻ ሲቀር ግን ልባቸውን በክሕደት የከፈቱ ሰዎች በእሱ ላይ ከአላህ ቁጣ አለባቸው። ለእነርሱም ታላቅ ቅጣት አላቸው። ይህ ቅጣት እነርሱ ቅርቢቱን ሕይወት ከመጨረሻይቱ በመምረጣቸው ምክንያትና አላህ ከሓዲያንን ሕዝቦች የማያቀና በመኾኑ ነው። እነዚያ እነርሱ በልቦቻቸው፤ በዓይኖቻቸውና በጆሮቻቸውም ላይ አላህ ያተመባቸው ናቸው። እነዚያም ዝንጉዎች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። እነርሱ በመጨረሻይቱ ዓለም ከሳሪዎቹ እነርሱ ለመኾናቸው ጥርጥር የለም።

ከንብ ምዕራፍ (106) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በአማር ኢብኑ ያሲር ምክንያት ነው የወረደው። ምክንያቱም የመካ ካፊሮች አባቱን ያሲርን እናቱን ሱመያ ጋር ሱሐይብ ቢላልንና ሳሊም አብረው ያዟቸው። ሱመያን በሁለት ግመሎች መካከል አስረዋት በሰንከሌ ወግተው ገደሏት። ባሏን ያሲርንም ገደሉት። እነህ ሁለት ሰዎች በኢስላም የመጀመሪያዎቹ የህይወት መስዋዕትነት ከፋዮች ናቸው። ዓማር ግን እነሱ የጠየቁትን በቃሉ ብቻ ከውስጥ ሳያምንበት ተገዶ ተናገረና ከእነሱ እጅ አመለጠ። ለነብዩም «ዓማር ከፈረ» ተብሎ ተናገራቸው። ነብዩ ግን «ዓማር ከራስ ፀጉሩ እስከ እግር ጥፍሩ ጫፍ እምነቱ ተቀላቅሎታል» በማለት መሰከሩለት። ከዚያም ወደ ነብዩ እያለቀሰ መጣ። ነብዩ አይኖቹን እያበሱለት ከዚህ በኋላም መልሰው ካስቸገሩህ በልላቸው አሉት። በዚህ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

ثُمَّ إِنَّ رَبَّكَ لِلَّذِينَ هَاجَرُواْ مِنۢ بَعۡدِ مَا فُتِنُواْ ثُمَّ جَٰهَدُواْ وَصَبَرُوٓاْ
إِنَّ رَبَّكَ مِنۢ بَعۡدِهَا لَغَفُورٞ رَّحِيمٞ ١١٠

**110.** ከዚያ ጌታህ ለእነዚያ ከተፈተኑ በኋላ ለተሰደዱት ከዚያ ለታገሉትና ለታገሡት መሐሪ፣ አዛኝ ነው። ጌታህ ከፈተናዋ በኋላ በእርግጥ መሐሪና አዛኝ ነውና።

ከንብ ምዕራፍ (110) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ ሰዎች «ወደ መዲና ካልተሠደዱ በስተቀር ኢስላምቻው ተቀባይነት የለውም» ሲባሉና እነሱም ተደናግጠው «የቀረ ይቅር» ብለው ሲወጡ ሙሽሪኮች ተከታትለው ስለመለሷቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ አልጀውዚና ዋሒዲ)

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (103-110) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ እንዴት አድርጎ ነብዩ ከሙሽሪኮች ተንኮል አደጋ እንደተከላከላቸው፤
2. የአላህን አያዎች የሚያስተባብሉ ሁሉ አላህን ፍራቻ የሚነፍጉ መሆናቸውንና አማኞች የእርሱን ተአምራት የማያስተባሉ ስለ መሆናቸው፤
3. በሀይለኛ የጠላት ኃይል ስቃይ የሚደርስበትና ግፍ የሚፈፅምበት ግለሰብ ራሱን ለማዳን በምላሱ ብቻ የኩፍርን ቃል ቢናገር በልቡ እስካልተቀበለው ድረስ ወንጀል የሌለበትና የሚፈቀድለት ስለ መሆኑ እንማራለን።

۞ يَوۡمَ تَأۡتِي كُلُّ نَفۡسٖ تُجَٰدِلُ عَن نَّفۡسِهَا وَتُوَفَّىٰ كُلُّ نَفۡسٖ مَّا عَمِلَتۡ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ ﴿١١١﴾

**111.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ነፍስ ሁሉ ከራሷ ላይ የምትከራከር ሆና የምትመጣበትን ነፍስም ሁሉ የሠራችውን ዋጋ የምትቀበልበትን ቀን (አስታውስ)። እነርሱም ፍፁም አይበደሉም።

وَضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلٗا قَرۡيَةٗ كَانَتۡ ءَامِنَةٗ مُّطۡمَئِنَّةٗ يَأۡتِيهَا رِزۡقُهَا رَغَدٗا مِّن كُلِّ مَكَانٖ فَكَفَرَتۡ بِأَنۡعُمِ ٱللَّهِ فَأَذَٰقَهَا ٱللَّهُ لِبَاسَ ٱلۡجُوعِ وَٱلۡخَوۡفِ بِمَا كَانُواْ يَصۡنَعُونَ ﴿١١٢﴾ وَلَقَدۡ جَآءَهُمۡ رَسُولٞ مِّنۡهُمۡ فَكَذَّبُوهُ فَأَخَذَهُمُ ٱلۡعَذَابُ وَهُمۡ ظَٰلِمُونَ ﴿١١٣﴾

**112-113.** አላህ ፀጥተኛ የረካች ሲሳይዋ ሰፊ ሆኖ ከየስፍራው ይመጣላት የነበረችውንና በአላህ ፀጋዎች የካደችውን አላህም ይሠሩት* በነበሩት ኃጢአት የረሀብንና የፍርሀትን ቅጣቶች ያቀመሳትን ከተማ (መካን) ምሳሌ አደረገ። ከእነርሱም ውስጥ የሆነ መልዕክተኛም በእርግጥ መጣላቸው። አስተባበሉትም እነርሱም በዳዩች ሆነው ቅጣቱ ያዛቸው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «የጀሃነም እሳትን ተመልክቻለሁ በውስጧ አብዛሃኞዎቹ ከሓዲያንና ምስጋና ቢስ ሴቶች ናቸው» ሶሓባዎችም «በአላህ ከሓዲያን ናቸው?» ሲሉ ጠየቁ። እሳቸውም «ባሎቻቸው መልካም ውለታ ሲውሉላቸው ምስጋና ቢሶች ናቸው። ለሚስትህ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ መልካም ውለታ ብትውልላትና አንዳች ነገር ባንተ ላይ ብትመለከት «ምንም አይነት መልካም ነገር ካንተ በኩል አይቼ አላውቅም» ትላለች»

فَكُلُواْ مِمَّا رَزَقَكُمُ ٱللَّهُ حَلَٰلٗا طَيِّبٗا وَٱشۡكُرُواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ إِن كُنتُمۡ إِيَّاهُ تَعۡبُدُونَ ﴿١١٤﴾ إِنَّمَا حَرَّمَ عَلَيۡكُمُ ٱلۡمَيۡتَةَ وَٱلدَّمَ وَلَحۡمَ ٱلۡخِنزِيرِ وَمَآ أُهِلَّ لِغَيۡرِ ٱللَّهِ بِهِۦۖ فَمَنِ ٱضۡطُرَّ غَيۡرَ بَاغٖ وَلَا عَادٖ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿١١٥﴾

**114-115.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይ የተፈቀደና ንፁሕ ሲሆን ብሉ። የአላህንም ፀጋ እርሱን የምትገዙት ከሆናችሁ አመስግኑት። በእናንተ ላይ እርም ያደረገው በክትንና ደምን የአሳማን ሥጋ ያንንም በሚታረድ ጊዜ በእርሱ ላይ ከአላህ ስም ሌላ የተነሳበትን ብቻ ነው። አመፀኛና ወሰን አላፊ ሳይሆን ከእነዚህ አንዱን ለመብላት የተገደደ ሰው ይፈቀድለታል። አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና።

وَلَا تَقُولُواْ لِمَا تَصِفُ أَلْسِنَتُكُمُ ٱلْكَذِبَ هَٰذَا حَلَٰلٌ وَهَٰذَا حَرَامٌ لِّتَفْتَرُواْ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَۚ
إِنَّ ٱلَّذِينَ يَفْتَرُونَ عَلَى ٱللَّهِ ٱلْكَذِبَ لَا يُفْلِحُونَ ﴿١١٦﴾ مَتَٰعٌ قَلِيلٌ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿١١٧﴾

**116-117.** (ከሓዲያን ሆይ)፤ በአላህ ላይ ውሸትን ልትቀጣጥፉ ምላሶቻችሁ በሚመጥኑት ውሸት ይህ የተፈቀደ ነው ይህ ደግሞ እርም ነው አትብሉ። እነዚያ በአላህ ላይ ውሸትን የሚቀጣጥፉ ክፍሎች በፍፁም አይድኑም። ጥቂት መጣቀም ብቻ አለላቸው። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

وَعَلَى ٱلَّذِينَ هَادُواْ حَرَّمْنَا مَا قَصَصْنَا عَلَيْكَ مِن قَبْلُۖ
وَمَا ظَلَمْنَٰهُمْ وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمْ يَظْلِمُونَ ﴿١١٨﴾

**118.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእነዚያ አይሁድ በሆኑት ሰዎች ላይ ከአሁን በፊት በአንተ ላይ የተረከነውን ነገር እርም አድርገንባቸዋል። እኛም አልበደልናቸውም። ግን ነፍሶቻቸውን ይበድሉ ነበሩ።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (111-118) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. ስደት ለአላህ ሃይማኖት ብሎ ሂጅራ ማድረግ ሸርጡ (መስፈርቱ) የተሟላ ጂሀድና ትዕግስት ታላላቅ የኢስላማዊ ህይወት መገለጫ ተግባራት ስለመሆናቸው፤
2. የመጨረሻዋን ቀን ማስታወስና ለእርሷም መዘጋጀት ግዴታ ስለመሆኑ፤
3. ምሳሌዎች ምን ያህል በአዋቂዎች አዕምሮ ላይ ለውጥን እንደሚያመጡ፤
4. የአላህን ፀጋ መካድ የፀጋውን ሰጪ አላህን በማስቆጣትና በማስቀየም ፀጋው እንዲወገድ የሚያደርግ ስለመሆኑ፤
5. ነብዩ (ﷺ) ባስተማሩት መሰረት አለመስራት የአላህን ቁጣ ሊያመጣ የሚችል ስለመሆኑ፤
6. የአላህን ፀጋ በምስጋና መቀበል ግዴታ ስለመሆኑ፤
7. ሰዎች እንዳይበሏቸው ከአላህ ጎዳና ማዕቀብ የተጣለባቸው የምግብ አይነቶች ምን ምን እንደሆኑ የተከለከሉ ምግቦችን መቼና በምን አይነት ሁኔታ መመገብ እንደሚፈቀድ፤
8. በቂ ሸሪዓዊ መረጃ ሳይዙ ነገሮችን ሀራም ወይም ሀላል እንደሆኑ አድርጎ ማቅረብ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
9. በአላህ ላይ መቅጠፍና መዋሸት እጅግ ከባድ ወንጀል ከመሆኑም ባሻገር ሰው በዚህ ወንጀሉ ምክንያት ብዙ መልካም እድሎች የሚያመልጡት መሆኑን እንማራለን።

ثُمَّ إِنَّ رَبَّكَ لِلَّذِينَ عَمِلُواْ ٱلسُّوٓءَ بِجَهَٰلَةٍ ثُمَّ تَابُواْ مِنۢ بَعْدِ ذَٰلِكَ وَأَصْلَحُوٓاْ إِنَّ رَبَّكَ مِنۢ
بَعْدِهَا لَغَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١١٩﴾

**119.** ከዚያ ጌታህ ለእነዚያ በስህተት መጥፎን ለሠሩትና ከዚያ ከዚህ በኋላ ለተፀፀቱ ሥራቸውንም ላበጁ ጌታህ ከእርሷ በኋላ በእርግጥ መሓሪና አዛኝ ነው።

إِنَّ إِبْرَٰهِيمَ كَانَ أُمَّةً قَانِتًا لِّلَّهِ حَنِيفًا وَلَمْ يَكُ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٢٠﴾ شَاكِرًا لِّأَنْعُمِهِۚ ٱجْتَبَىٰهُ وَهَدَىٰهُ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿١٢١﴾ وَءَاتَيْنَٰهُ فِى ٱلدُّنْيَا حَسَنَةًۖ وَإِنَّهُۥ فِى ٱلْءَاخِرَةِ لَمِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿١٢٢﴾ ثُمَّ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ أَنِ ٱتَّبِعْ مِلَّةَ إِبْرَٰهِيمَ حَنِيفًاۖ وَمَا كَانَ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿١٢٣﴾

**120-123.** ኢብራሂም ለአላህ ታዛዥ፣ ወደ ቀጥተኛ ሃይማኖት ተዘንባይ ህዝብ ነበር። ከአጋሪዎችም አልነበረም። ለፀጋዎቹ አመስጋኝ ነበር። መረጠው። ወደ ቀጥተኛውም መንገድ መራው። በቅርቢቱ ዓለም በጎን ነገር ሰጠነው። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም በእርግጥ ከመልካሞቹ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፣ ከዚያ ወደ አንተ የኢብራሂምን ሃይማኖት ቀጥተኛ ሲሆን ተከተል። ከአጋሪዎቹም አልነበረም ማለትን አወረድን።

إِنَّمَا جُعِلَ ٱلسَّبْتُ عَلَى ٱلَّذِينَ ٱخْتَلَفُوا۟ فِيهِۚ وَإِنَّ رَبَّكَ لَيَحْكُمُ بَيْنَهُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ فِيمَا كَانُوا۟ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ﴿١٢٤﴾

**124.** ሰንበት (በቅዳሜ ቀን መስራት ክልክል) የተደረገው በእነዚያ በእርሱ በተለያዩበት ሰዎች ላይ ብቻ ነው። ጌታህም በትንሳኤ ቀን ይለያዩበት በነበሩት ነገር በመካከላቸው በእርግጥ ይፈርዳል።

ٱدْعُ إِلَىٰ سَبِيلِ رَبِّكَ بِٱلْحِكْمَةِ وَٱلْمَوْعِظَةِ ٱلْحَسَنَةِۖ وَجَٰدِلْهُم بِٱلَّتِى هِىَ أَحْسَنُۚ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعْلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِۦ وَهُوَ أَعْلَمُ بِٱلْمُهْتَدِينَ ﴿١٢٥﴾

**125.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ (በለዘብተኛ ቃል) ሰዎችን ጥራ። በዚያችም እርሷ በመልካም በሆነችው ዘዴ ተከራከራቸው። ጌታህ ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው ዐዋቂ ነው። እንደዚሁም እርሱ ቅን የሆኑትን ሰዎች ዐዋቂ ነው።

وَإِنْ عَاقَبْتُمْ فَعَاقِبُوا۟ بِمِثْلِ مَا عُوقِبْتُم بِهِۦۖ وَلَئِن صَبَرْتُمْ لَهُوَ خَيْرٌ لِّلصَّٰبِرِينَ ﴿١٢٦﴾ وَٱصْبِرْ وَمَا صَبْرُكَ إِلَّا بِٱللَّهِۚ وَلَا تَحْزَنْ عَلَيْهِمْ وَلَا تَكُ فِى ضَيْقٍ مِّمَّا يَمْكُرُونَ ﴿١٢٧﴾ إِنَّ ٱللَّهَ مَعَ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوا۟ وَّٱلَّذِينَ هُم مُّحْسِنُونَ ﴿١٢٨﴾

**126-128.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ብትበቀሉም በእርሱ በተቀጣችሁበት ብጤ ተበቀሉ። ብትታገሱ ግን እርሱ ለታጋሾች*[1] በእርግጥ በላጭ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ታገስ። መታገስህ በአላህ ማስቻል ብቻ

እንጂ በግል አቅምህ አይደለም። በእነርሱም ላይ (ባያምኑ) አትተከዝ። በአንተ ላይ በሚመክሩት ተንኮልም በጭንቀት ውስጥ አትሁን። አላህ ከእነዚያ እሱን ከሚፈሩትና✳2 ከእነዚያም እነርሱ ከመልካም ሥራ ከሆኑት ሰዎች ጋር ነውና።

✳1 (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከሰዎች በሚሰማው መጥፎ ንግግር ከአላህ በላይ በጣም የሚታገስ የለም። ሰዎች ለአላህ ልጅ አለው ይላሉ። ዳሩ ግን እሱ ጤንነትንና ሃብትን ይሰጣቸዋል።

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንደወትሯቸው አንዳንድ ነገሮችን እንደሚያከፋፍሉ አንድን ነገር አከፋፈሉ። ከአንሷር ጎሳ የሆነ አንድ ሰው «በአላህ እምላለሁ! በዚህ ክፍፍል ላይ የአላህ ደስታ አልተፈለገበትም» ሲል ተናገረ። እኔም «ለነብዩ ይህን ነገር በእርግጥ እነግራቸዋለሁ» አልኩና በቀጥታ ወደ ነብዩ (ﷺ) ስሄድ ከሶሓቦቻቸው ጋር ተቀምጠው ነበር። ቀስ ብዬ በምስጢር ነገርኳቸው። ይህ አይነቱ አነጋገር ለእሳቸው እጅግ ከባድ ነበር። በዚህ የተነሳ የፊታቸው ቀለም ተለዋወጠ። እኔም ምነው ሳልነግራቸው ብቀር እስከምል ድረስ በጣም ተቆጡና «ሙሳ ከዚህ የበለጠ ነገር ተነግሮታል። ግን ታጋሽ ሆኗል።»አሉ።

✳2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የማናችሁም ሥራዎች ከጀሃነም እሳት አያድናችሁም» አሉ። ሰዎችም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርስዎንም ቢሆን?» ሲሉ ጠየቋቸው። እሳቸውም «እኔም ብሆን አላህ በርህራሄው እስካልከበበኝ ድረስ አሉ።

ከንብ ምዕራፍ ከ (125-127) ኛ ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በኡሁድ ጦርነት ቀን በተጋደሉ ሙስሊሞች መካከል አስቀያሚ ነገር በማየታቸውና በተለይ የሀምዛ ሆድ መቀደድና አፍንጫው ተተልትሎ ጆሮዎቹ ተቆርጠው ሲያዩት ሴቶች ባያዝኑና ወይም ከኔ በኋላ እንደግዴታ የማይታይ ቢሆን ኖሮ አላህ ከአውሬዎች ሆድ እንዲቀሰቀሰው እንዳለ እተወው ነበር። በጌታዬ ይሁንብኝ ከአቡ ሱፍያን ሠባ ሠዎችን እገላለሁ ብለው ስለነበር ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ኢብኑ ከሲር፣ ዳሩል ቁጥኒ፣ ሓኪም፣ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)።

**ከንብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (119-128) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የተውባህ በር ለማንኛውም የሰው ልጅ ክፍት ስለመሆኑ፤
2. ቁርኣን ተውሒድን ማወጁንና የተውሒድ ቀንደኛ አራማጁን የነብዩ ኢብራሂም ታሪክ በሰፊው መዘገቡን፤
3. አይሁድ ሰንበት በማለት ቅዳሜን ማክበራቸው የአላህን ቁጣ በእነሱ ላይ መዋሉን እንጂ ፀጋውን እንደማያመለክት፤
4. ወደ አላህ ጎዳና ጥሪ ማድረግና በዳዕዋ ላይ ፀንቶ መዘወተር ግዴታ ስለመሆኑ፤
5. የዳዕዋ ዘዴዎች የተለያዩ መሆናቸውን ማስተማርና ዋና ዋናዎቹን የሚያስተምር ቁርኣናዊ አንቀፅ መመልከት
6. ማንም ሰው ለደረሰበት ጥቃትና ዝርፊያ ተመጣጣኝ የሆነ ቅጣት መቅጣት የሚችል ስለ መሆኑና ሆኖም መታገሱና በይቅርታ ማለፍ የበለጠና ተመራጭ መሆኑን፤
7. አላህ ለፈራህያን በሙሉ ድልን በመስጠትና ድጋፍን በማጎናፀፍ ረገድ ዘወትር ከጎናቸው የማይለይ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የንብ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (17)
# የሌሊት ጉዞ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ኢስራእ)

سُورَةُ الإِسْرَاءِ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (111) ናቸው።
### የሱረቱ አል ኢስራእ መግቢያ

የሱብሓን ምዕራፍ፤ የበኒ ኢስራኢል ልጆች ምዕራፍም ይባላል።

አላህ ከማይገቡ ነገሮች ሁሉ የፀዳ መሆኑን አውስቶ የነብዩን (ﷺ) የሰማይ ጉዞ፤ ከዚያ የሙሳን መልዕክተኝነትና የኢስራኢል ልጆችን ሁኔታ፤ ቁርኣን ሰዎችን በማቅናት ዙሪያ ያለው ሚና ከፍተኛ መሆኑን፤ በሌሊትና በቀን ውስጥ ያሉትን ተዐምራት፤ ሰዎች በዚህ ዓለም በሰሩት ሥራ የቂያማ ዕለት የሚሰጣቸው ምንዳ ከተግባራቸው አኳያ መሆኑን፤ ለሰዎች መበላሸት ምክንያቱ ምን እንደሆነና ሰዎች በተግባራቸው ያላቸውን ልዩ ልዩ ባህሪያት ይዘረዝራል። ስለ ወላጆች ክብር በማንሳት ምክር ይሰጣል። ሰዎች ንብረታቸውን በተመለከተ ያላቸው ሁኔታ ምን እንደሚመስል ካብራራ በኋላ ማህበረሰቡ ሁሉ የሚያስፈልገውን አስርቱን ትዕዛዛት አከታትሎ ያስተምራል። ከሓዲያን በመላኢኮች ጉዳይ ላይ ያደረጉትን ቅጥፈት በዝርዝር ያጋልጥና አላህ ምስጋና የሚገባው መሆኑን በድጋሚ አስምሮና በትኩረት አስተምሮ የካሐዲያንን ክህደት በመጠቆም ምእመናን ጠቃሚ ምክሮችን ይለግሳል። ከሓዲያንን በተመለከተ በዚህ ዓለምም ሆነ በአኼራ እንዴት እንደሚሆኑ የሰው ልጆች አባትና የሰይጣኖች አባት እነማን እንደሆኑ አብራርቶ አጋሪዎች ሰይጣንን ከመከተል እንዲጠነቀቁ ያሳስባል። የሰው ልጅ ክብር ያለው ፍጡር መሆኑንም በሰፊው ይገልፃል። የቂያማ ቀንን ቅጣት አውስቶ ከዚያ ከሓዲያን ነብዩን (ﷺ) ከአላማቸው ለማደናቀፍ ሙከራ ማድረጋቸውንና አላህ ነብዩን (ﷺ) እንዴት በአቋማቸው እንዲፀኑ እንዳጽናናቸው በተጨማሪም ብዙ ምክሮችንም እንደለገሳቸው ይተነትናል።

ከዚህ በመቀጠልም የቁርኣንን ትልቅነት፤ ስለ ሩህ (ነፍስ) ና ሚስጥሯ፤ ሰዎችም ሆኑ ጋኔኖች ቁርኣንን የመሰለ ማምጣት እንደማይችሉ፤ አላህ ግን የፈለገውን ተአምር ማምጣትና ማሳየት እንደሚችል፤ ይህ ዓይነት ባህሪያት ያለው ጌታ አላህ ዝንተዓለም ሊወደስና ሊከበር እንደሚገባው በመግለጽ መልዕክቱን ያጠቃልላል። ይህ አንቀፅ ያንን የአላህ ተዐምር የሆነውንና ለነብዩም ትልቅ ክብር የነበረውን የሌሊት ጉዞ ይዘግባል። ይኸውም በዚያች ባጭር ጊዜ ከመካ በይተል መቅዲስ ከዚያ ወደ ሰማይ በመሄድ ያን ሁሉ ተዐምር ማየታቸውን ያስተምራል። ቁርኣን የአላህ ቃል ነው። እሱን ማንበቡ ብቻ እንኳን የአላህ አምልኮ ይገለፅበታል። ከእሱው ጀምሮ ወደ እሱው ይመለሳል። በፊደሉም ሆነ በድምፁ ተናግሮበታል። ቁርኣን መልአኩ ጂብሪል ከአላህ ሰምቶት ከዚያ ወደ ነብዩ (ﷺ) አድርሶታል። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ቁርኣን ከአላህ የተወረደ የአላህ ቃል መሆኑ።

እዚህ ላይ ሊነሳ የሚገባው ጥያቄ ሀዲስን ትተን በቁርኣን ብቻ መብቃቃት ይቻላል? የሚለው ነው መልሱም በአጭሩ፡ አይቻልም ነው። ምክንያቱም አላህ ራሱ ሀዲስን እንድንይዝ፡- «መልዕክተኛው የሰጣችሁን) ማንኛውንም ነገር ያዙት። ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ»። በማለት አዟልናል። ሀዲስ ደግሞ የቁርኣን ማብራሪያ ነው። የኢስላም ህግጋቱም ሆነም የስነ ስርአቱ ዝርዝሩ ያለ ሐዲስ አይታወቅም። ነብዩ (ﷺ) አህመድና አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ፡- «አዋጅ፤ ቁርኣንና መሰሉን ተሰጥቻለሁ። አዋጅ፤ አንዳንድ የጠገቡ ሰዎች በትራሳቸው ላይ ተደግፈው ይህን ቁርኣን ያዙ። እሱ ሐላል ያደረገላችሁን ሐላል በሉ። ሐራም ያደረገባችሁንም ሐራም በሉ። ለማለት ይቀርባሉ» ብለዋል።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَـٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

سُبْحَـٰنَ ٱلَّذِىٓ أَسْرَىٰ بِعَبْدِهِۦ لَيْلًا مِّنَ ٱلْمَسْجِدِ ٱلْحَرَامِ إِلَى ٱلْمَسْجِدِ ٱلْأَقْصَا ٱلَّذِى بَـٰرَكْنَا
حَوْلَهُۥ لِنُرِيَهُۥ مِنْ ءَايَـٰتِنَآ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلْبَصِيرُ ١

**1.** ጥራት ለዚያ ባሪያውን*1 (ሙሐመድን) ከተከበረው የሐረም መስጊድ ወደዚያ ዙሪያውን ወደባረክነው ሩቁ (አል አቅሷ) መስጊድ በሌሊት ለወሰደው ጌታ ለአላህ ይሁን። ይህን ያደረግን ተአምራታችንን ልናሳየው*2 ነው። እነሆ አላህ ሰሚና ተመልካች ነው።

*1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «ቁረይሾች ወደ ሰማይ ማረጌን ሳያምኑኝ ቀርተው ባለበት ጊዜ በሒጅር ላይ ቆም አላህም በይተል. መቅዲስን እየሩሳሌምን ገለፀልኝ ወደርሱም እየተመለከትኩ ስለርሱ እገልፅላቸው ጀመር»

*2 ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ የኢስራእ ጉዞ ባደረጉበት ሌሊት አንደኛው ወተት ሌላኛው ወይን ጠጅ የያዙ ሁለት ዋንጫዎች ቀረቡላቸው። አዩዋቸውና ወተቱትን ያዙ። ጅብሪልም፡- «ተፈጥሯዊን መንገድ ላመላከትህ አላህ ምስጋና ይድረሰው። ወይን ጠጁም መርጠህ ቢሆን ኖሮ ተከታዮችህ ጥመት ውስጥ በተዘፈቁ ነበር» አለ።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከ (1) ኛው አንቀፅ ከምናገኘው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የኢስራእና የሚዕራጅ ተዐምር አላህ ለነብዩ (ﷺ) የሰጣቸው ተዐምር መሆኑን፤
2. ለአላህ አገልጋይነት ትልቅ ማዕረግ እንደሆነ፤
3. የሁለቶችም መስጊዶች ክብርና ማዕረግ የቱን ያህል እንደሆነ፤
4. ሻም የተባለው ሀገር ምን ያህል የተባረከ መሆኑን፤
5. አላህ ለነብዩ (ﷺ) ያሳያቸው አያሌ ተዐምር ለእምነት ፅናትን የሚቸር፤ በአቋም ላይ የሚያጠናክር መሆኑን እንማራለን።

وَءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَـٰبَ وَجَعَلْنَـٰهُ هُدًى لِّبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ أَلَّا تَتَّخِذُوا۟ مِن دُونِى وَكِيلًا ٢
ذُرِّيَّةَ مَنْ حَمَلْنَا مَعَ نُوحٍ ۚ إِنَّهُۥ كَانَ عَبْدًا شَكُورًا ٣ وَقَضَيْنَآ إِلَىٰ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ
فِى ٱلْكِتَـٰبِ لَتُفْسِدُنَّ فِى ٱلْأَرْضِ مَرَّتَيْنِ وَلَتَعْلُنَّ عُلُوًّا كَبِيرًا ٤ فَإِذَا جَآءَ وَعْدُ أُولَىٰهُمَا
بَعَثْنَا عَلَيْكُمْ عِبَادًا لَّنَآ أُو۟لِى بَأْسٍ شَدِيدٍ فَجَاسُوا۟ خِلَـٰلَ ٱلدِّيَارِ ۚ وَكَانَ وَعْدًا مَّفْعُولًا ٥
ثُمَّ رَدَدْنَا لَكُمُ ٱلْكَرَّةَ عَلَيْهِمْ وَأَمْدَدْنَـٰكُم بِأَمْوَٰلٍ وَبَنِينَ وَجَعَلْنَـٰكُمْ أَكْثَرَ نَفِيرًا ٦
إِنْ أَحْسَنتُمْ أَحْسَنتُمْ لِأَنفُسِكُمْ ۖ وَإِنْ أَسَأْتُمْ فَلَهَا ۚ فَإِذَا جَآءَ وَعْدُ ٱلْـَٔاخِرَةِ لِيَسُـۥٓـُٔوا۟
وُجُوهَكُمْ وَلِيَدْخُلُوا۟ ٱلْمَسْجِدَ كَمَا دَخَلُوهُ أَوَّلَ مَرَّةٍ وَلِيُتَبِّرُوا۟ مَا عَلَوْا۟ تَتْبِيرًا ٧

**2-7.** ለሙሳም (ተውራት የተባለውን) መጽሐፍ ሰጠነውና ለኢስራኤል ልጆች መሪ አደረግነው። «ከእኔ ሌላ ወኪል (መጠጊያ) አድርጋችሁ ማንንም አትያዙ»። ስንልም አዘዝናቸው። እናንተ "ከኑህ ጋር በመርከቧ ላይ የጫንናቸው አማኝ ዘሮች ሆይ (አላህን ተገዙ)፤ ኑህ በእርግጥ አምላኩን አመስጋኝ ባሪያ ነበር አልናቸው። ለኢስራኤል ልጆችም፡ "በምድር ላይ ሁለት ጊዜ ጥፋት ትፈጽማላችሁ። አለቅጥም አምባገነን ትሆናላችሁ።" ስንል በመጽሐፉ ውስጥ ገለጽን። ከሁለቱ ጊዚያቶች የመጀመሪያው ጥፋት መፈፀሚያ ወቅቱ በደረሰ ጊዜ ለእኛ የሆኑን የበረታ ኃይል ያላቸውን ባሮቻችንን ላክንባችሁ። እነርሱም ቤቶችን ሁሉ አሰሱ (በረበሩ)። ይህ መፈፀሙ የማይቀር ውሳኔ ነበር። (የኢስራኤል ልጆች ሆይ!) ከዚያ በእነርሱ ላይ የድል አድራጊነትን እድል ሰጠናችሁ። ገንዘብንና ወንዶች ልጆችን ለገስንላችሁ። በሰው ኃይልም ብዙ አደረግናችሁ።* መልካም ነገሮችን ብትሠሩ ለነፍሶቻችሁ መልካምን ሠራችሁ። መጥፎንም ብትሠሩ በነፍሶቻችሁ ላይ ነው። የሌላይቱ ጥፋት ቀጠሮ በደረሰ ጊዜ ፊቶቻችሁን ሊያስከፉ መስጊዱንም በመጀመሪያ ጊዜ እንደገቡት ሊገቡ ያሸነፉትንም ሁሉ ፈጽመው ማጥፋትን እንዲያጠፉ እንልካቸዋለን።

✷ ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከ (2-7) ያሉት አናቅፅ ጥቅል መልዕክት፡-
ስለ ኢስራኢል ልጆችና የተሰጣቸውን ታላላቅ ፀጋ ማለትም ልጆች ሀብት በጠላት ድልን መቀዳጀት ከተሰጡ በኋላ ይህንን ሁሉ በመካድና በሌሎችም ጥፋታቸው ምክንያት በምድር ላይ ሁለት ጊዜ እንዲሰደዱ እንደተፈረደባቸውና የመጨረሻው የጥፋታቸው ዘመን በደረሰ ጊዜም ጠላቶቻቸውን በመላክ እንደሚያዋርዳቸውም ዝቶባቸዋል።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከ (2-7) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የኢስራኤል ልጆች ምን ያህል አጥፊዎች እንደነበሩ፤
2. ልጆች የአባታቸውን ፀጋ ማመስገን ግዴታ እንደሆነ፤
3. አሁንም መልሰው ካጠፉ የአላህ ቅጣት እንደሚመለስባቸው መዛቱን እንማራለን።

عَسَىٰ رَبُّكُمْ أَن يَرْحَمَكُمْ ۚ وَإِنْ عُدتُّمْ عُدْنَا ۘ وَجَعَلْنَا جَهَنَّمَ لِلْكَافِرِينَ حَصِيرًا ﴿٨﴾

**8.** (የኢስራኤል ልጆች ሆይ፣ በመጽሐፉም አልን) ብትፀፀቱ ጌታችሁ ሊያዝንላችሁ ይከጀላል። ወደ ማጥፋት እንደገና ብትመለሱ እኛም ወደ ቅጣቱ እንመለሳለን። ገሀነምንም ለከሓዲያን ሁሉ ማሰሪያ አድርገናል።

إِنَّ هَٰذَا الْقُرْآنَ يَهْدِي لِلَّتِي هِيَ أَقْوَمُ وَيُبَشِّرُ الْمُؤْمِنِينَ الَّذِينَ يَعْمَلُونَ الصَّالِحَاتِ أَنَّ
لَهُمْ أَجْرًا كَبِيرًا ﴿٩﴾ وَأَنَّ الَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِالْآخِرَةِ أَعْتَدْنَا لَهُمْ عَذَابًا أَلِيمًا ﴿١٠﴾ وَيَدْعُ
الْإِنسَانُ بِالشَّرِّ دُعَاءَهُ بِالْخَيْرِ ۖ وَكَانَ الْإِنسَانُ عَجُولًا ﴿١١﴾

**9-11.** ይህ ቁርኣን ወደዚያች እርሷ በሁሉ ነገር ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል። እነዚያን በጎ የሚሠሩትንም ለእነርሱ ታላቅ ምንዳ ያላቸው መኾኑን ያበስራል። እነዚያም በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣትን አዘጋጅተንላቸዋል። ሰው መልካምን ነገር እንደሚለምን ሁሉ መጥፎንም ነገር ይለምናል። ሰው ቸኳይ ነውና።

وَجَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ ءَايَتَيۡنِۖ فَمَحَوۡنَآ ءَايَةَ ٱلَّيۡلِ وَجَعَلۡنَآ ءَايَةَ ٱلنَّهَارِ مُبۡصِرَةٗ لِّتَبۡتَغُواْ
فَضۡلٗا مِّن رَّبِّكُمۡ وَلِتَعۡلَمُواْ عَدَدَ ٱلسِّنِينَ وَٱلۡحِسَابَۚ وَكُلَّ شَيۡءٖ فَصَّلۡنَٰهُ تَفۡصِيلٗا ١٢

**12.** ሌሊትንና ቀንን ለችሎታችን ምልክቶች አደረግን። የሌሊትን ምልክትም አበስን የቀን ምልክት የምታሳይ አደረግን። ይህም የኾነበት ከአላህ ትርፍን ልትፈልጉበትና የዓመታትንም ቁጥርና ሒሳብን ታውቁበት ዘንድ ነው። ነገሩንም ሁሉ ለያይተን ዘረዘርነው።

وَكُلَّ إِنسَٰنٍ أَلۡزَمۡنَٰهُ طَٰٓئِرَهُۥ فِي عُنُقِهِۦۖ وَنُخۡرِجُ لَهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ كِتَٰبٗا يَلۡقَىٰهُ مَنشُورًا ١٣
ٱقۡرَأۡ كِتَٰبَكَ كَفَىٰ بِنَفۡسِكَ ٱلۡيَوۡمَ عَلَيۡكَ حَسِيبٗا ١٤

**13-14.** ሰውን ሁሉ (በራሪውን) ሥራውን በአንገቱ ላይ አስያዝነው። ለእርሱም በትንሣኤ ቀን የተዘረጋ ኾኖ የሚያገኘው የኾነን መጽሐፍ እናወጣለታለን። ከዚያ መጽሐፍህን አንብብ። ዛሬ በአንተ ላይ ተቆጣጣሪነት በነፍስህ ብቻ በቃ ይባላል።

مَّنِ ٱهۡتَدَىٰ فَإِنَّمَا يَهۡتَدِي لِنَفۡسِهِۦۖ وَمَن ضَلَّ فَإِنَّمَا يَضِلُّ عَلَيۡهَاۚ وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٞ وِزۡرَ
أُخۡرَىٰۗ وَمَا كُنَّا مُعَذِّبِينَ حَتَّىٰ نَبۡعَثَ رَسُولٗا ١٥

**15.** በቀናው መንገድ የተመራ ሰው ሁሉ የሚመራው ለእራሱ ብቻ ነው። ከቀናው መንገድ የተሳሳተም ሰው የመሳሳቱ ጉዳት በእርሱ ላይ ብቻ ነው። ተሸካሚይም ነፍስ የሌላይቱን ኃጢአት አትሸከምም። መልዕክተኛን እስከምንልክ ድረስ ማንንም የምንቀጣ አይደለንም።

ከሌሊት ጉዞ (15) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ቀደም ሲል እናታችን ኸዲጃ ነብዩን (ﷺ) ስለ ከሓዲያን ልጆች ጉዳይ ጠይቀዋቸው የእሳት እንደሆኑ ነግረዋቸው ነበር። ለሁለተኛ ጊዜ ሲጠይቋቸውና «አላህ ያውቃል» ባሉበት ጊዜ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ከዚያም በኋላ የጀነት ናቸው በማለት ነገሯቸው። ቡኻሪ፤ ሙስሊምና አቡ ዳውድ ዘግበውታል።

وَإِذَآ أَرَدۡنَآ أَن نُّهۡلِكَ قَرۡيَةً أَمَرۡنَا مُتۡرَفِيهَا فَفَسَقُواْ فِيهَا فَحَقَّ عَلَيۡهَا ٱلۡقَوۡلُ
فَدَمَّرۡنَٰهَا تَدۡمِيرٗا ﴿١٦﴾ وَكَمۡ أَهۡلَكۡنَا مِنَ ٱلۡقُرُونِ مِنۢ بَعۡدِ نُوحٖۗ
وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ بِذُنُوبِ عِبَادِهِۦ خَبِيرَۢا بَصِيرٗا ﴿١٧﴾

**16-17.** ማንኛዋንም ከተማ ለማጥፋት በፈለግን ጊዜ ባለ ፀጋዎችዋን እናዛቸዋለን፡፡ በውስጧም ያምፃሉ፡፡ በእርሷም ላይ የቅጣት ቃሉ ይፈፀምባታል፡፡ ከዚያ (ማውደምን እናወድማታለን)፡፡ ማጥፋትንም እናጠፋታለን፡፡ ከኑሕም በኋላ ከየክፍለ ዘመናት ሰዎች ያጠፋናቸው ብዙዎች ናቸው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የባሮቹንም ኃጢአቶች ውስጠ ዐዋቂ ተመልካች መሆን በጌታህ ብቻ በቃ፡፡

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (8-17) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህ ቀጠሮ ተፈጻሚነት፤
2. ይህን መሰል ታሪክ ነብይ እንጂ ማንም መናገር ባለመቻሉ የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
3. ሥራ ለሰሪው የሚለውን አባባል ሐቀኝነት ማረጋገጥ፤
4. የቁርኣንን ትልቅነት ማረጋገጥ፤
5. የሰው ልጅ በቁርኣን ከመመራቱ በፊት ያለው ባህሪ ምን እንደሚመስል፤
6. ሌትና ቀን የአላህ ተአምራት መሆናቸውን፤
7. የሂሳብ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን፤
8. የቀደና ቀደርን እምነት አስፈላጊነት ማጠናከር፤
9. ሙቶ መነሳት ሐቅ መሆኑን ማረጋገጥ፤
10. በትንሳኤ እለት በሚሰጠው አምላካዊ ፍትህ ትንሽም ቢሆን መበደል እንደማይኖር ማረጋገጥ፤
11. አላህ ህዝቦችን በየጊዜው በጥፋታቸው ያጠፋ ቢሆንም ካስጠነቀቀና ምክንያቶችን ካስጨረሰ በኋላ መሆኑን፤
12. በብዛት በዱንያ መዝናናትና መደሰት ተገቢ አለመሆኑን ማስጠንቀቅን እንማራለን፡፡

مَّن كَانَ يُرِيدُ ٱلۡعَاجِلَةَ عَجَّلۡنَا لَهُۥ فِيهَا مَا نَشَآءُ لِمَن نُّرِيدُ ثُمَّ جَعَلۡنَا لَهُۥ جَهَنَّمَ يَصۡلَىٰهَا
مَذۡمُومٗا مَّدۡحُورٗا ﴿١٨﴾ وَمَنۡ أَرَادَ ٱلۡأٓخِرَةَ وَسَعَىٰ لَهَا سَعۡيَهَا وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَأُوْلَٰٓئِكَ كَانَ
سَعۡيُهُم مَّشۡكُورٗا ﴿١٩﴾ كُلّٗا نُّمِدُّ هَٰٓؤُلَآءِ وَهَٰٓؤُلَآءِ مِنۡ عَطَآءِ رَبِّكَۚ وَمَا كَانَ عَطَآءُ رَبِّكَ
مَحۡظُورًا ﴿٢٠﴾ ٱنظُرۡ كَيۡفَ فَضَّلۡنَا بَعۡضَهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۚ وَلَلۡأٓخِرَةُ أَكۡبَرُ دَرَجَٰتٖ وَأَكۡبَرُ
تَفۡضِيلٗا ﴿٢١﴾ لَّا تَجۡعَلۡ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَتَقۡعُدَ مَذۡمُومٗا مَّخۡذُولٗا ﴿٢٢﴾ ۞وَقَضَىٰ رَبُّكَ أَلَّا
تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّآ إِيَّاهُ وَبِٱلۡوَٰلِدَيۡنِ إِحۡسَٰنًاۚ إِمَّا يَبۡلُغَنَّ عِندَكَ ٱلۡكِبَرَ أَحَدُهُمَآ أَوۡ كِلَاهُمَا فَلَا تَقُل

لَّهُمَآ أُفّٖ وَلَا تَنۡهَرۡهُمَا وَقُل لَّهُمَا قَوۡلٗا كَرِيمٗا ﴿٢٣﴾ وَٱخۡفِضۡ لَهُمَا جَنَاحَ ٱلذُّلِّ مِنَ ٱلرَّحۡمَةِ
وَقُل رَّبِّ ٱرۡحَمۡهُمَا كَمَا رَبَّيَانِي صَغِيرٗا ﴿٢٤﴾ رَّبُّكُمۡ أَعۡلَمُ بِمَا فِي نُفُوسِكُمۡۚ إِن تَكُونُواْ
صَٰلِحِينَ فَإِنَّهُۥ كَانَ لِلۡأَوَّٰبِينَ غَفُورٗا ﴿٢٥﴾

**18-25.** ጊዜያዊቱን ዓለም (በሥራው) የሚፈልግ ሰው ሁሉ ለእርሱ ከእርሷ ውስጥ የፈለግነውን ፀጋ ለምንፈልገው ሰው ብቻ እናስቸኩልለታለን። ከዚያ ለእርሱ ገሀነምን መኖሪያ አድርገንለታል። ተወቃሽና ከአላህ እዝነት የተባረረ ሆኖ ይገባባታል*። የመጨረሻይቱን ዓለም የፈለገ እና እርሱ አማኝ ሆኖ ለእርሷ ተገቢ የሆነን ሥራ የሠራ ሰው ደግሞ እነዚህ ሥራቸው የተመሰገነ ይሆናል። ሁሉንም እነዚህን እና እነዚያን ከጌታህ ስጦታ በዚህ ዓለም እንጨምርላቸዋለን። የጌታህ ስጦታ በዚች ዓለም ክልክል አይደለም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከፊላቸውን በከፊሉ ላይ እንዴት እንዳስበለጥን ተመልከት። የመጨረሻይቱም አገር በማዕረጎች በጣም የከበረችና በመብለጥም የላቀች ናት። (የሰው ልጅ ሆይ)፤ ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ። የተወቀስክ፤ ረዳት የሌለህ ትሆናለህና። (የሰው ልጅ ሆይ)፤ ጌታህ እንዲህ ሲል አዘዘ። እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ ለወላጆቻችሁም መልካምን ሥሩ፤ በአንተ ዘንድ ሆነው ከወላጆችህ አንዳቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ኡፍ እንኳን አትበላቸው። አትገላምጣቸውም። ለእነርሱም መልካምን ቃል ብቻ ተናገራቸው። የሰው ልጅ ሆይ፤ ለሁለቱ የመተናነስ ክንፍን ዝቅ አድርግላቸው። ጌታዬ ሆይ፤ በሕጻንነቴ በርህራሄ እንዳሳደጉኝ ሁሉ ለእነርሱም እዘንላቸው በል። (ሰዎች ሆይ)፤ ጌታችሁ በነፍሶቻችሁ ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ዐዋቂ ነው። ታዛዦችም ብትሆኑ ወይም ብታጠፉ እርሱ ለተመላሾች ሁሉ መሓሪ ነው።

* የተፍሲር ምሁራን እዚህ ላይ «አትቅረቡ» የሚለው ቃል ዝሙትን አትፈፅሙ ከማለት ይበልጥ ጥልቀት አለው ይላሉ። እውነትም ዝሙት መንገድነቱ ከፋ። ምክንያቱም፡-

1. ዝሙት ክብርን ያጠፋል፤ ስምን ያቆሽሻል፤ ነውረኛ ያደርጋል።
2. ዝሙት በሰዎች ዘንድ ጥላቻን ያመጣል።
3. ዝሙት ሰውየውን ባይገለው እንኳን በሽተኛ ያደርገዋል።
4. ዝሙት ቤተሰብን ይበትናል፤ ፍቅር ያሳጣል። ልጆች ያለ እንክብካቤ እንዲያድጉ ብሎም ለመጥፎ ባህሪ እንዲጋለጡ ያደረጋል።
5. ዝሙት ዘርን ያደባልቃል። ቤተሰብ ያልሆነን ዘመድ ያለ አግባብ ያስወርሳል። ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አንድ ባልደረባቸው አንዲት የተማረከች እርጉዝ ሴት ባሪያ ለግንኙት አስቦ ሲጠይቃቸው «አብሮት የሚቀበር እርግማን ልረግመው ነበር እንዴት የማይፈቀድለትን ያስወርሳል። እንዴት የማይፈቀድለትን አገልጋይ ያደርገዋል» ብለዋል።

«ዘመድ ያልሆነን ሰው ዘመድ አስመስላ በመሀላቸው ያስገባች ሴት በአላህ ዘንድ ምንም አይደለችም። ወደ ጀነቱም አያስገባትም። በአይኑ እያየው ልጁን የካደ ሰው አላህ ከርሱ ይደበቃል። የቂያማ ዕለትም በህዝብ ፊት ያዋርደዋል»ብለዋል።

6. ዝሙት ሀላፊነት የጎደለው እንስሳዊ ግንኙነት ነው።
7. ዝሙት ግድያን ከሚያስፋፉት ወንጀሎች አንዱ ነው። ምክንያቱም ለክብሩና ለስሙ የሚጓጓ ሰው መግደልን እንደመፍትሄ ሊቆጥረው ይችላል።
8. ዝሙት የማህበረሰቡን ትስስር ያፈራርሳል። የጎዳና ተዳዳሪ ልጆችን ያበራክታል። እንኳን አባት እናታቸውን የማያውቁ ትውልዶች እንዲበዙ ያደርጋል።
9. ዝሙት ጭንቀትና ሐሳብ ያበዛል። ዝሙት ለሰሪው ቀርቶ ለዘመድና ለጓደኛ አንገት ያስደፋል።
10. ዝሙት ለተላላፊ በሽታዎች መስፋፋት ዋና መንገድ ነው።
11. ዝሙት የአላህን ቁጣ ያመጣል። ዐብዱላህ ኢብኑ መስዑድ አትናገሩት "ዝሙት በግልፅ የሚፈፀምበት መንደር አላህ ሊያጠፋው የፈለገ መንደር ነው። "ብለዋል።
12. የዝሙት መስፋፋት የትንሳኤ ቀን መቅረብን ከሚያመለክቱ ብዙ ነገሮች አንዱ ነው። ነብዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፡- «ከትንሳኤ ቀን ምልክቶች መካከል የእውቀት ማነስና፤ የድንቁርና መስፋፋት፤ አስካሪ ነገር እንደልብ መጠጣት፤ ዝሙት በይፋ መፈፀም፤ የወንዶች ቁጥር ማነስና ከሴቶች ብዛት የተነሳ አንድ ወንድ ለሐምሳ ሴቶች አስተዳዳሪ መሆን ነው ብለዋል»

ዝሙት ብዙ ደረጃዎች አሉት፡- የጐረቤት ሚስት ላይ የሚፈፀመው ዝሙት ነብዩ (ﷺ) ከሺርክና ሰውን ከመግደል ቀጥለው ማውሳታቸው በቂ ነው። ከዚህ ይበልጥ በዘመዱ ሚስት ከሆነ ከዚያም ራሱ ሽማግሌ ከሆነ ወንጀሉ እየጨመረ ይሄዳል።

وَءَاتِ ذَا ٱلۡقُرۡبَىٰ حَقَّهُۥ وَٱلۡمِسۡكِينَ وَٱبۡنَ ٱلسَّبِيلِ وَلَا تُبَذِّرۡ تَبۡذِيرًا ﴿٢٦﴾ إِنَّ ٱلۡمُبَذِّرِينَ
كَانُوٓاْ إِخۡوَٰنَ ٱلشَّيَٰطِينِۖ وَكَانَ ٱلشَّيۡطَٰنُ لِرَبِّهِۦ كَفُورٗا ﴿٢٧﴾ وَإِمَّا تُعۡرِضَنَّ عَنۡهُمُ ٱبۡتِغَآءَ رَحۡمَةٖ
مِّن رَّبِّكَ تَرۡجُوهَا فَقُل لَّهُمۡ قَوۡلٗا مَّيۡسُورٗا ﴿٢٨﴾ وَلَا تَجۡعَلۡ يَدَكَ مَغۡلُولَةً إِلَىٰ عُنُقِكَ وَلَا
تَبۡسُطۡهَا كُلَّ ٱلۡبَسۡطِ فَتَقۡعُدَ مَلُومٗا مَّحۡسُورًا ﴿٢٩﴾ إِنَّ رَبَّكَ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقۡدِرُۚ
إِنَّهُۥ كَانَ بِعِبَادِهِۦ خَبِيرَۢا بَصِيرٗا ﴿٣٠﴾

**26-30.** (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ለዝምድና ባለቤት ሁሉ ተገቢ መብቱን ስጥ። ለምስኪንና ለመንገደኛም እንዲሁ መብቱን ስጥ። በሁሉም ነገር ላይ ማባከንንም አታባክን። አባካኞች የሰይጣናት ወንድሞች ናቸውና። ሰይጣን ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው። ከጌታህ የምትከጅላትን ፀጋ ለማምጣት በማሰብ ከእነርሱ ብትዞር ለእነርሱ (ለወላጆች) ልዝብን ቃል ተናገራቸው። እጅህን ወደ አንገትህ ታጥፋ የታሠረች አታድርግ። መዘርጋትንም ሁሉ አትዘርጋት። የተወቀስክና የተቆጨህ ትኾናለህና። ጌታህ ሲሳይን ለሚፈልገው ሰው ያሰፋል። ለሚፈልገው ሰውም ያጠባል። እርሱ በባሮቹ ሁኔታ ውስጥ ዐዋቂ፤ ተመልካች ነውና።

وَلَا تَقۡتُلُوٓاْ أَوۡلَٰدَكُمۡ خَشۡيَةَ إِمۡلَٰقٖۖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُهُمۡ وَإِيَّاكُمۡۚ إِنَّ قَتۡلَهُمۡ كَانَ خِطۡـٔٗا كَبِيرٗا ﴿٣١﴾
وَلَا تَقۡرَبُواْ ٱلزِّنَىٰٓۖ إِنَّهُۥ كَانَ فَٰحِشَةٗ وَسَآءَ سَبِيلٗا ﴿٣٢﴾ وَلَا تَقۡتُلُواْ ٱلنَّفۡسَ ٱلَّتِي حَرَّمَ ٱللَّهُ
إِلَّا بِٱلۡحَقِّۗ وَمَن قُتِلَ مَظۡلُومٗا فَقَدۡ جَعَلۡنَا لِوَلِيِّهِۦ سُلۡطَٰنٗا فَلَا يُسۡرِف فِّي ٱلۡقَتۡلِۖ إِنَّهُۥ كَانَ
مَنصُورٗا ﴿٣٣﴾ وَلَا تَقۡرَبُواْ مَالَ ٱلۡيَتِيمِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ حَتَّىٰ يَبۡلُغَ أَشُدَّهُۥۚ وَأَوۡفُواْ
بِٱلۡعَهۡدِۖ إِنَّ ٱلۡعَهۡدَ كَانَ مَسۡـُٔولٗا ﴿٣٤﴾ وَأَوۡفُواْ ٱلۡكَيۡلَ إِذَا كِلۡتُمۡ وَزِنُواْ بِٱلۡقِسۡطَاسِ ٱلۡمُسۡتَقِيمِۚ
ذَٰلِكَ خَيۡرٞ وَأَحۡسَنُ تَأۡوِيلٗا ﴿٣٥﴾ وَلَا تَقۡفُ مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٌۚ إِنَّ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡبَصَرَ
وَٱلۡفُؤَادَ كُلُّ أُوْلَٰٓئِكَ كَانَ عَنۡهُ مَسۡـُٔولٗا ﴿٣٦﴾ وَلَا تَمۡشِ فِي ٱلۡأَرۡضِ مَرَحًاۖ إِنَّكَ لَن تَخۡرِقَ
ٱلۡأَرۡضَ وَلَن تَبۡلُغَ ٱلۡجِبَالَ طُولٗا ﴿٣٧﴾ كُلُّ ذَٰلِكَ كَانَ سَيِّئُهُۥ عِندَ رَبِّكَ مَكۡرُوهٗا ﴿٣٨﴾
ذَٰلِكَ مِمَّآ أَوۡحَىٰٓ إِلَيۡكَ رَبُّكَ مِنَ ٱلۡحِكۡمَةِۗ وَلَا تَجۡعَلۡ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَتُلۡقَىٰ
فِي جَهَنَّمَ مَلُومٗا مَّدۡحُورًا ﴿٣٩﴾

**31-39.** (ሰዎች ሆይ)፣ ልጆቻችሁን ድህነትን በመፍራት አትግደሉ። እኛ እንመግባቸዋለን። እናንተንም እንመግባለን። እነርሱን መግደል ታላቅ ኃጢአት ነውና። (ሰዎች ሆይ)፣ ዝሙትን አትቅረቡ። እርሱ በእርግጥ መጥፎ ሥራ ነውና። መንገድነቱም ከፋ፣ ያቺን አላህ ያከበራትን ነፍስ ያለ ሕግ አትግደሉ። የተበደለ ሆኖ የተገደለ ሰው ሁሉ ለዘመዱ በገዳዩ ላይ ስልጣንን አድርገናል። በመግደል ወሰንን አይለፍ። እርሱ እገዛ ያለው ነውና። (ሰዎች ሆይ)፣ የየቲምን ገንዘብ የብርታቱን ጊዜ እስኪደርስ ድረስ በዚያች እርሷ መልካም በሆነች ሁኔታ እንጂ አትቅረቡ። በቃል ኪዳናችሁም ሙሉ። ቃል ኪዳን የሚጠየቁበት ጉዳይ ነውና። (ሰዎች ሆይ)፣ በሰፈራችሁም ጊዜ ስፍርን ሙሉ። በትክክለኛው ሚዛንም መዝኑ። ይህ መልካም ነገር ነው። መጨረሻውም ያማረ ነው። (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ለአንተ በእርሱ እውቀት የሌለህን ነገር አትከተል። መስሚያ ጆሮ፤ ማያ አይን፤ ማሰቢያ ልብም እነዚህ ሁሉ ባለቤታቸው ከእነርሱ ተጠያቂ ነውና። የሰው ልጅ ሆይ፣ በምድር ላይ የተንበጣረርክ ሆነህ አትሂድ። አንተ ፈጽሞ ምድርን አትሰረጉድምና። በርዝመትም ፈጽሞ ጋራዎችን አትደርስምና። (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ይህ ሁሉ መጥፎው ከጌታህ ዘንድ የተጠላ ነው። (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ይህ ጌታህ ከጥበብ ወደ አንተ ካወረደው ነገር ነው። (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ አታድርግ። የተወቀስክ፤ የተባረርክ ሆነህ በገሀነም ውስጥ ትጣላለህና።

أَفَأَصۡفَىٰكُمۡ رَبُّكُم بِٱلۡبَنِينَ وَٱتَّخَذَ مِنَ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ إِنَٰثًاۚ إِنَّكُمۡ لَتَقُولُونَ قَوۡلًا عَظِيمٗا ﴿٤٠﴾
وَلَقَدۡ صَرَّفۡنَا فِي هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ لِيَذَّكَّرُواْ وَمَا يَزِيدُهُمۡ إِلَّا نُفُورٗا ﴿٤١﴾

**40-41.** (ጣኦታዊያን ሆይ)፣ ጌታችሁ በወንዶች ልጆች መረጣችሁና ከመላዕክት ሴቶችን ልጆች ለራሱ ያዘን? እናንተ ከባድ ቃል በእርግጥ ትናገራላችሁ። ይገሰፁ ዘንድ በዚህ ቁርኣን ውስጥ ደጋግመን በእርግጥ ገለጽን። ለእነርሱ ግን ከትክክለኛው መንገድ መበርገግን እንጂ ሌላን አይጨምርላቸውም።

قُل لَّوۡ كَانَ مَعَهُۥٓ ءَالِهَةٞ كَمَا يَقُولُونَ إِذٗا لَّٱبۡتَغَوۡاْ إِلَىٰ ذِي ٱلۡعَرۡشِ سَبِيلٗا ﴿٤٢﴾
سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يَقُولُونَ عُلُوّٗا كَبِيرٗا ﴿٤٣﴾

**42-43.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱ እንደሚሉት ከእርሱ ጋር ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ ያን ጊዜ ወደ ዐርሹ ባለቤት መንገድን በፈለጉ ነበር በላቸው። ጥራት ይገባው። አላህ እነርሱ ከሚሉት ነገር ሁሉ ከፍ ያለን ልቅና ላቀ።

تُسَبِّحُ لَهُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ ٱلسَّبۡعُ وَٱلۡأَرۡضُ وَمَن فِيهِنَّۚ وَإِن مِّن شَيۡءٍ إِلَّا يُسَبِّحُ بِحَمۡدِهِۦ
وَلَٰكِن لَّا تَفۡقَهُونَ تَسۡبِيحَهُمۡۚ إِنَّهُۥ كَانَ حَلِيمًا غَفُورٗا ﴿٤٤﴾

**44.** ሰባቱ ሰማያትና ምድር እንዲሁም በውስጣቸው ያለው ሁሉ እርሱን ያጠራሉ። ከነገሩ ሁሉ እሱን ከማመስገን ጋር የሚያጠራው እንጂ አንድም የለም። (ሰዎች ሆይ)፣ ማጥራታቸውን ግን አታውቁትም። እርሱ ታጋሽ፤ መሓሪ ነው።

وَإِذَا قَرَأۡتَ ٱلۡقُرۡءَانَ جَعَلۡنَا بَيۡنَكَ وَبَيۡنَ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِ حِجَابٗا مَّسۡتُورٗا ﴿٤٥﴾
وَجَعَلۡنَا عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ أَكِنَّةً أَن يَفۡقَهُوهُ وَفِيٓ ءَاذَانِهِمۡ وَقۡرٗاۚ وَإِذَا ذَكَرۡتَ رَبَّكَ فِي ٱلۡقُرۡءَانِ
وَحۡدَهُۥ وَلَّوۡاْ عَلَىٰٓ أَدۡبَٰرِهِمۡ نُفُورٗا ﴿٤٦﴾ نَّحۡنُ أَعۡلَمُ بِمَا يَسۡتَمِعُونَ بِهِۦٓ إِذۡ يَسۡتَمِعُونَ إِلَيۡكَ
وَإِذۡ هُمۡ نَجۡوَىٰٓ إِذۡ يَقُولُ ٱلظَّٰلِمُونَ إِن تَتَّبِعُونَ إِلَّا رَجُلٗا مَّسۡحُورًا ﴿٤٧﴾ ٱنظُرۡ كَيۡفَ
ضَرَبُواْ لَكَ ٱلۡأَمۡثَالَ فَضَلُّواْ فَلَا يَسۡتَطِيعُونَ سَبِيلٗا ﴿٤٨﴾

**45-48.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቁርኣንን ባነበብክ ጊዜ በአንተና በእነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም በማያምኑት ሰዎች መካከል የሚሸሸግን ግርዶሽ አድርገናል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እንዳያውቁት በልቦቻቸው ላይ ሽፋንን፤ በጆሮቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን አደረግን። ጌታህንም ብቻውን ሆኖ በቁርኣን ባወሳኸው ጊዜ የሚሸሹ ሆነው በጀርባዎቻቸውም ላይ ይዞራሉ። እኛ ወደ አንተ በሚያዳምጡ፣ በሚንሾካሾኩ፣ በዳዮች እርስ በእርሳቸው የተደገመበትን ሰው እንጂ አትከተሉም በሚሉ ጊዜ በእርሱ የሚያዳምጡበትን ምክንያት ዐዋቂ ነን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምሳሌዎችን ለአንተ እንዴት እንዳደረጉልህና እንደ ተሳሳቱ ተመልከት። ወደ እውነቱ ለመድረስ ትክክለኛውን መንገድ ለመከተል አይችሉም።

وَقَالُوٓاْ أَءِذَا كُنَّا عِظَٰمٗا وَرُفَٰتًا أَءِنَّا لَمَبۡعُوثُونَ خَلۡقٗا جَدِيدٗا ﴿٤٩﴾ ۞قُلۡ كُونُواْ حِجَارَةً أَوۡ
حَدِيدًا ﴿٥٠﴾ أَوۡ خَلۡقٗا مِّمَّا يَكۡبُرُ فِي صُدُورِكُمۡۚ فَسَيَقُولُونَ مَن يُعِيدُنَاۖ قُلِ ٱلَّذِي فَطَرَكُمۡ
أَوَّلَ مَرَّةٖۚ فَسَيُنۡغِضُونَ إِلَيۡكَ رُءُوسَهُمۡ وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هُوَۖ قُلۡ عَسَىٰٓ أَن يَكُونَ قَرِيبٗا ﴿٥١﴾
يَوۡمَ يَدۡعُوكُمۡ فَتَسۡتَجِيبُونَ بِحَمۡدِهِۦ وَتَظُنُّونَ إِن لَّبِثۡتُمۡ إِلَّا قَلِيلٗا ﴿٥٢﴾

**49-52.** አሉም፡- እንዴት? አጥንቶችና ብስብሶች በሆን ጊዜ እኛ እንደገና አዲስ ፍጥረት ሆነን በእርግጥ ተቀስቃሾች ነን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ድንጋዮች ወይም ብረት ሁኑ በላቸው። ወይም በልቦቻችሁ ውስጥ የሚተልቅን ፍጥረት ሁኑ መቀስቀሳችሁ አይቀርም የሚመልሰንም ማነው? ይላሉ። ያ በመጀመሪያ ጊዜ የፈጠራችሁ ነው በላቸው። ወደ አንተም ራሶቻቸውን ይነቀንቃሉ። እርሱም መቼ ነው? ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱ በቅርብ ቀን ሊሆን ይቻላል በላቸው። እርሱም የሚጠራችሁንና አላህን አመስጋኞቹ ሆናችሁ ጥሪውን የምትቀበሉበት፤ ጥቂትን ቀኖች እንጂ ያልቆያችሁ መሆናችሁን የምትጠራጠሩበት ቀን ነው በላቸው።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (18-52) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *በሁለቱም ዓለም መደሰት በስራ ላይ የተመሰረተ መሆኑን፤*
2. *የዱንያ ልፋት ንግድ፤ እርሻ፤ አምራችነት ወ. ዘ. ተ መሆኑን፤*
3. *የአኼራ ንግድ በአላህ ማመን፤ መልካም ሥራ መስራት፤ ከሽርክ እና ከተለያዩ ወንጀሎች ነጻ መሆን መሆኑን፤*

4. አላህ ዱንያን ለሚወዳቸውም ሆነ ለማይወዳቸው ሰዎች እንደሚሰጥ፤ አኼራን ግን ለሚወዳቸው ሰዎች ብቻ እንደሚሰጥ፤
5. አላህ የሰጠውን ማንም እንደማይከለክል፤
6. አላህን በብቸኝነት ማምለክና ለወላጆች መልካም መዋል የያንዳንዳችን ግዴታ መሆኑን፤
7. ለወላጆች መታዘዝና ለእነርሱ ምህረትን ከአላህ መለመን በያንዳንዳችን ላይ ግዴታ መሆኑን፤
8. አላህን መጠባበቅ እና ምንም አይነት መጥፎ ነገርን በውስጥ ደብቆ መያዝ እንደሌለብን፤
9. መጥፎ ነገር ላይ የወደቀና ተውባህ ያደረገ ሰው አላህ ምህረትን እንደሚለግሰው፤
10. ዘመድ፤ ድሆችና የመንገድ ልጆች መብታቸው መጠበቅ እንዳለበት፤
11. ገንዘብ ማባካን ማለት አላህ በከለከለው ነገር ላይ ማዋል ማለት እንደሆነ፤
12. መልካም ተስፋ መስጠት እንደስጦታ እንደሚቆጠር፤
13. ንፉግነትና አባካኝነት ክልክል መሆኑንና መካከለኛነትና ፍትሃዊነት ያለውን ክብር፤
14. አላህ ለግማሹ አስፋፍቶ ለሌላው ሲያጠብ ያለው ረቂቅ ጥበብና ሚስጥር፤
15. ነውር ወይም ድህነትን ፈርቶ ልጆችን መግደል ክልክል መሆኑን፤
16. ለዝሙት በር ከፋች ነገሮችን በስሜት መመልከት፤ ከባዕድ ሴት ወይም ወንድ ጋር ማውራትና ሰውነቷን (ሰውነቱን) መንካት እንደ ዝሙት ተግባር እንደሚቆጠር፤
17. አላህ እንዳይገደሉ ያከበራቸውን ነፍሳት አለመግደል፤
18. የየቲምን ገንዘብ መብላትና ማባከን እንዲሁም ችላ ብሎ እንዲከስር ማድረግ ክልክል መሆኑን፤
19. በቃል ኪዳንና በውል መገኘት ግዴታ መሆኑን፤
20. ስፍርንና ሚዛንን በአግባቡ መፈፀም እንደሌለብን፤
21. በስፍርና በሚዛን የአላህን ሕግ ያከበረ ሊያገኘው የሚችለው ረድኤትና በረካ፤
22. ያለ እውቀት ምንም ነገር መስራት ክልክል መሆኑንና ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ እንደሚያመዝንና አላህን ልጅ አለው ረዳት አለው ማለት ክልክል ስለመሆኑ፤
23. ኩራት ስለመከልከሉና የኩራተኞች ቅጣት ምን እንደሚመስል፤
24. በእነዚህ አናቅፅ ውስጥ ከሃያ አምስት ያላነሱ ጠቃሚ ትምህርቶች መኖራቸውን፤
25. እውነትን ለማውጣትና ለማስረዳት በሎጂካዊ ማስረጃዎች መጠቀም ተገቢ ተግባር ስለመሆኑ፤
26. ሱብሃነላህ እያሉ አላህን ማጥራት ተገቢ ስለመሆኑ፤
27. አንድን ነገር መውደድ ህሊናን እንደሚያሳውርና ልቦናን እንደሚደፍን፤
28. አጋሪዎች ተውሒድን እንደሚጠሉ፤
29. አጋሪዎች በነብዩ (ﷺ) እና በቁርኣን ያፌዙ እንደነበር፤
30. አጋሪዎች ነብዩን (ﷺ) በሲህርና በጥንቆላ ከዚያም በእብደት ስማቸውን ያጎድፏቸው እንደነበር፤
31. ከሓዲያንን ሙቶ መነሳትን በተመለከተ የነበራቸው የከረረ አቋም፤
32. አላህ ነብዩን (ﷺ) እነዚያን የከረረ አቋም የነበራቸውን ሰዎች እንኳን በመልካም ባህሪ ማስተማር እንዳለባቸው ያዘዛቸው መሆኑን፤
33. የውይይት ስርዓት ምን መምሰል እንደለበት መማር፤
34. የቅርቢቱ አለም ኑሮ ኑሮ የቱንም ያህል ቢረዝም ከአኼራ ጋር ሲነፃፀር ኢምንት እንደሚሆን እንማራለን።

وَقُل لِّعِبَادِي يَقُولُوا۟ ٱلَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ۚ إِنَّ ٱلشَّيْطَٰنَ يَنزَغُ بَيْنَهُمْ ۚ إِنَّ ٱلشَّيْطَٰنَ كَانَ لِلْإِنسَٰنِ عَدُوًّا مُّبِينًا ﴿٥٣﴾ رَّبُّكُمْ أَعْلَمُ بِكُمْ ۖ إِن يَشَأْ يَرْحَمْكُمْ أَوْ إِن يَشَأْ يُعَذِّبْكُمْ ۚ وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ عَلَيْهِمْ وَكِيلًا ﴿٥٤﴾

**53-54.** ለባሮቼም በላቸው፡፡ ሁልጊዜም ያችን እርሷ መልካም የሆነችውን ቃል ይናገሩ፡፡ ሰይጣን በመካከላቸው ያበላሻልና፡፡ ሰይጣን ለሰው ልጆች ግልጽ ጠላት ነውና፡፡ (ሰዎች ሆይ)፤ ጌታችሁ በእናንተ ሁኔታ ዐዋቂ ነው፡፡ ቢፈልግ ያዝንላችኋል፡፡ ቢፈልግ ይቀጣችኋል (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእነርሱ ላይ ሀላፊ ሆነህ አላከንህም፡፡ አታስገድዳቸውም፡፡

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (53) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- (ሀ) ዑመር ኢብኑልኸጣብ አንድ ዐረብ ሰድቧቸው ስለ ነበር በይቅርታ እንዲያልፉት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ቁርጢቢ)፡፡

(ለ) ከሓዲያን ያስቸግሯቸው የነበሩ ሱሃቦች ጉዳዩን ለነብዩ ስሞታ ተናግረው ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ዋሒዲ እና ኢብኑ አልጀውዚ)

وَرَبُّكَ أَعْلَمُ بِمَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۗ وَلَقَدْ فَضَّلْنَا بَعْضَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ عَلَىٰ بَعْضٍ ۖ وَءَاتَيْنَا دَاوُۥدَ زَبُورًا ﴿٥٥﴾

**55.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ በሰማያትና በምድር ያለውን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡ ከፊሉን ነብያት በከፊሉ ላይ አብልጠናል፡፡ ዳውድን ዘቡርን ሰጥተነዋል፡፡

قُلِ ٱدْعُوا۟ ٱلَّذِينَ زَعَمْتُم مِّن دُونِهِۦ فَلَا يَمْلِكُونَ كَشْفَ ٱلضُّرِّ عَنكُمْ وَلَا تَحْوِيلًا ﴿٥٦﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ يَدْعُونَ يَبْتَغُونَ إِلَىٰ رَبِّهِمُ ٱلْوَسِيلَةَ أَيُّهُمْ أَقْرَبُ وَيَرْجُونَ رَحْمَتَهُۥ وَيَخَافُونَ عَذَابَهُۥٓ ۚ إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ كَانَ مَحْذُورًا ﴿٥٧﴾

**56-57.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ከእርሱ ሌላ አማልዕክት የምትሏቸውን ጥሩ ከናንተም ላይ ጉዳትን ማስወገድን ወደ ሌላ ማዞርንም አይችሉም በላቸው፡፡ እነዚያ እነርሱ የሚገዟቸው ማንኛቸውም (ወደ አላህ) በጣም ቀራቢያቸው ወደ ጌታቸው መቃረቢያን ሥራ ይፈልጋሉ፡፡ እዝነቱንም ይከጅላሉ ቅጣቱንም ይፈራሉ የጌታህ ቅጣት የሚፈራ ነውና፡፡

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (56) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ጋኔንን ያመልኩ የነበሩ ሰዎች ነበሩ፡፡ ጂኖቹ ሲሰልሙ ሰዎቹ ግን የነበሩበትን አምልኮት ይዘው በመቀጠላቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ኢብኑ ከሲር፤ ኢብኑ አልጀውዚ እና ሱዩጢ)

وَإِن مِّن قَرْيَةٍ إِلَّا نَحْنُ مُهْلِكُوهَا قَبْلَ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ أَوْ مُعَذِّبُوهَا عَذَابًا شَدِيدًا ۚ كَانَ ذَٰلِكَ
فِى ٱلْكِتَٰبِ مَسْطُورًا ﴿٥٨﴾ وَمَا مَنَعَنَآ أَن نُّرْسِلَ بِٱلْءَايَٰتِ إِلَّآ أَن كَذَّبَ بِهَا ٱلْأَوَّلُونَ ۚ وَءَاتَيْنَا
ثَمُودَ ٱلنَّاقَةَ مُبْصِرَةً فَظَلَمُوا۟ بِهَا ۚ وَمَا نُرْسِلُ بِٱلْءَايَٰتِ إِلَّا تَخْوِيفًا ﴿٥٩﴾ وَإِذْ قُلْنَا لَكَ إِنَّ رَبَّكَ
أَحَاطَ بِٱلنَّاسِ ۚ وَمَا جَعَلْنَا ٱلرُّءْيَا ٱلَّتِىٓ أَرَيْنَٰكَ إِلَّا فِتْنَةً لِّلنَّاسِ وَٱلشَّجَرَةَ ٱلْمَلْعُونَةَ فِى
ٱلْقُرْءَانِ ۚ وَنُخَوِّفُهُمْ فَمَا يَزِيدُهُمْ إِلَّا طُغْيَٰنًا كَبِيرًا ﴿٦٠﴾

**58-60.** አንዲትም ከተማ የለችም እኛ ከትንሳኤ ቀን በፊት አጥፊዎችዋ ወይም ብርቱን ቅጣት ቀጭዎችዋ ብንሆን እንጂ። ይህ በመጽሐፍ የተጻፈ ነው። ተዐምራትን ከመላክ የቀድሞዎቹ ሰዎች በእርሷ ማስተባበልና መጥፋት እንጂ ሌላ አልከለከለንም ለሠሙድም ግመልን ግልጽ ተዐምር ሆና ሰጠናቸው። በእርሷም በደሉ ተዐምራቶችንም ለማስፈራራት እንጂ አንልክም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለአንተም ጌታህ በእውቀቱ ሰዎችን ያካበበ መሆኑን በነገርንህ ጊዜ የሆነው (አስታውስ)። ያችንም በሌሊቱ ጉዞ በዓይንህ ያሳየንህን* ትርኢይት ለሰዎች ፈተና እንጂ አላደረግነውም። በቁርአንም የተረገመችውን ዛፍ እንደዚሁ ፈተና እንጂ አላደረግንም እናስፈራራቸዋለንም፤ታላቅንም ጥመት እንጂ አይጨምርላቸውም።

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (59) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የመካ ሰዎች የሶፋን ጋራ ወርቅ እንዲያደርጉላቸው፤ ጋራዎችን እንዲያስወግዱላቸውና እዝርዕት እንዲዘሩ መልዕክተኛውን ጠይቀዋቸው ስለነበር፤ አላህ «ከፈለክ የጠየቁትን እሰጥሀለሁ ነገር ግን ከዚያ በኋላ ከካዱ ያለፉት ህዝቦች ሁሉ እንደ ጠፉ ይጠፋሉ። ከፈለክ ደግሞ እንጠብቃቸውና ከመሀላቸው እንመርጣለን» ሲላቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (አህመድ፤ ጦበሪ፤ ኢብኑ ከሲር፤ ኢብኑልጀውዚ እና ሱዩጢ)

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (60) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- አላህ ቁረይሾችን ዘቁም በተባለው ዛፍ ሲያስፈራራ ጊዜ አቡ ጀህል ተነስቶ ሙሐመድ (ﷺ) የሚያስፈራራባችሁን ዛፍ አውቃችኋል በማለት ጠይቆ አላወቅንም ሲሉት ስጋ በእርጎ ማለት አይደል እንዴ በጌታዬ ይሁንብኝ እናድርጋለን ሲል ነው የወረደው። (ኢብኑ ከሲር፤ ኢብኑ አልጀውዚ እና ዋሒዲ)

* ነብዩ (ﷺ) በሌሊቱ ጉዟቸው ላይ የፈፀሟቸው ታላላቅና ግዙፍ የሆኑ ተግባራት ለምሳሌ በይተል መቅዲስ መሄድ፤ ወደ የሰባቱ ሰማይ መድረስና አያሌ ጉዳዩችን ማውራት እና ሌሎችንም መፈፀማቸው በአንድ ሌሊት ቀርቶ በአንድ ወር፤ በአንድ ዓመት እንኳን የማይፈፀም ድርጊቶችን ፈፅመው በመምጣታቸው እንኳን ቀደም ሲል በክህደት ላይ የነበሩ ይቅርና አንዳንድ አማኞችም ቢሆኑ እስከ መፈተን ደርሰዋል።

وَإِذۡ قُلۡنَا لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ قَالَ ءَأَسۡجُدُ لِمَنۡ خَلَقۡتَ
طِينٗا ﴿٦١﴾ قَالَ أَرَءَيۡتَكَ هَٰذَا ٱلَّذِي كَرَّمۡتَ عَلَيَّ لَئِنۡ أَخَّرۡتَنِ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ لَأَحۡتَنِكَنَّ
ذُرِّيَّتَهُۥٓ إِلَّا قَلِيلٗا ﴿٦٢﴾ قَالَ ٱذۡهَبۡ فَمَن تَبِعَكَ مِنۡهُمۡ فَإِنَّ جَهَنَّمَ جَزَآؤُكُمۡ جَزَآءٗ
مَّوۡفُورٗا ﴿٦٣﴾ وَٱسۡتَفۡزِزۡ مَنِ ٱسۡتَطَعۡتَ مِنۡهُم بِصَوۡتِكَ وَأَجۡلِبۡ عَلَيۡهِم بِخَيۡلِكَ وَرَجِلِكَ
وَشَارِكۡهُمۡ فِي ٱلۡأَمۡوَٰلِ وَٱلۡأَوۡلَٰدِ وَعِدۡهُمۡۚ وَمَا يَعِدُهُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ إِلَّا غُرُورًا ﴿٦٤﴾ إِنَّ عِبَادِي
لَيۡسَ لَكَ عَلَيۡهِمۡ سُلۡطَٰنٞۚ وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ وَكِيلٗا ﴿٦٥﴾

**61-65.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለመላዕክትም ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ የነበረውን ሁኔታ (አስታውስ)። ወዲያውም ሰገዱ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር ከጭቃ ለፈጠርከው ሰው እሰግዳለሁን? አለ። እስቲ ንገረኝ ይህ ያ፣ በእኔ ላይ ያበለጥከው ነውን? እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ብታቆየኝ ዘሮቹን ጥቂቶች ሲቀሩ ወደ ስህተት በእርግጥ እስባቸዋለሁ አለ። (አላህም) አለው፡- ሂድ ከእነርሱም የተከተለህ ገሀነም የተሟላች ቅጣት ስትሆን ምንዳችሁ ናት። ከእነርሱ የቻልከውንም ሰው በድምጽህ ገፋፋ። በእነርሱም ላይ በፈረሰኞችህ በእግረኞችህም ሆነህ ጋልብ። በገንዘቦቻቸውም በልጆቻቸውም ተጋራቸው። የተስፋ ቃል ግባላቸው። ሰይጣንም ማታለልን እንጂ ተስፋ ቃልን አይገባላቸውም። ንፁህ ባሮቼ ግን በእነርሱ ላይ ፈጽሞ ለአንተ ስልጣን የለህም። መጠጊያም በጌታህ በቃ።

رَّبُّكُمُ ٱلَّذِي يُزۡجِي لَكُمُ ٱلۡفُلۡكَ فِي ٱلۡبَحۡرِ لِتَبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِهِۦٓۚ إِنَّهُۥ كَانَ بِكُمۡ
رَحِيمٗا ﴿٦٦﴾ وَإِذَا مَسَّكُمُ ٱلضُّرُّ فِي ٱلۡبَحۡرِ ضَلَّ مَن تَدۡعُونَ إِلَّآ إِيَّاهُۖ فَلَمَّا نَجَّىٰكُمۡ إِلَى
ٱلۡبَرِّ أَعۡرَضۡتُمۡۚ وَكَانَ ٱلۡإِنسَٰنُ كَفُورًا ﴿٦٧﴾ أَفَأَمِنتُمۡ أَن يَخۡسِفَ بِكُمۡ جَانِبَ ٱلۡبَرِّ أَوۡ يُرۡسِلَ
عَلَيۡكُمۡ حَاصِبٗا ثُمَّ لَا تَجِدُواْ لَكُمۡ وَكِيلًا ﴿٦٨﴾ أَمۡ أَمِنتُمۡ أَن يُعِيدَكُمۡ فِيهِ تَارَةً أُخۡرَىٰ
فَيُرۡسِلَ عَلَيۡكُمۡ قَاصِفٗا مِّنَ ٱلرِّيحِ فَيُغۡرِقَكُم بِمَا كَفَرۡتُمۡ ثُمَّ لَا تَجِدُواْ لَكُمۡ عَلَيۡنَا
بِهِۦ تَبِيعٗا ﴿٦٩﴾ ۞وَلَقَدۡ كَرَّمۡنَا بَنِيٓ ءَادَمَ وَحَمَلۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ وَرَزَقۡنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ
وَفَضَّلۡنَٰهُمۡ عَلَىٰ كَثِيرٖ مِّمَّنۡ خَلَقۡنَا تَفۡضِيلٗا ﴿٧٠﴾

**66-70.** (ሰዎች ሆይ)፣ ጌታችሁ ያ፣ ከችሮታው ትፈልጉ ዘንድ መርከቦችን በባህር ላይ ለእናንተ የሚነዳላችሁ ነው። እነሆ እርሱ ለእናንተ አዛኝ ነውና። በባህሩ ውስጥ ሆናችሁ ጉዳት በደረሰባችሁ ጊዜ የምትጠሯቸው አማልዕክት ሁሉ ከእርሱ ከአላህ በስተቀር ይጠፋሉ። ወደ የብስም በማድረስ ባዳናችሁ ጊዜ እምነትን ትተዋላችሁ። ሰው ሲባል በጣም ከሓዲ ነው። (ሰዎች ሆይ)፣ የየብሱን በኩል ምድርን በናንተ መገልበጡን ወይም ጠጠርን የያዘ ነፍስን በእናንተ ላይ መላኩን ከዚያ ለእናንተ ጠባቂ አለማግኘታችሁን አትፈሩምን? ወይስ ሌላ ጊዜ ወደ እርሱ ወደ ባህር የሚመልሳችሁ ወዲያውኑ በእናንተ ላይ ብርቱን ነፋስ የሚልክ በክህደታችሁም ምክንያት የሚያሰምጣችሁ መሆኑን ከዚያ በእኛ ላይ በእርሱ ተከታይነት ረዳትን ለእናንተ የማታገኙ መሆናችሁን አትፈሩምን? የአደምን ልጆች በእርግጥ ከሌላው ፍጡር አከበርናቸው። በየብስና በባህርም አሳፈርናቸው ከመልካሞችም ሲሳዮች ሰጠናቸው ከፈጠርናቸው ፍጡሮች በብዙዎቹ ላይ ማብለጥን አበለጥናቸው።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (53-66) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኢስላምን የሚያስተምር ሰው የተማሪውን ሞራልና ስሜት የሚያቆስል ነገር መናገር እንደማይገባው፤
2. ሰይጣን ሁልጊዜም በሰዎች መካከል ሰላምን ማየት ስለማይፈልግ ቁጣ የሚወልዱ ክርክሮችና ጭቅጭቆችን እንደሚፈጥር፤
3. በውይይት ዓለም ጥሩ አባባል ማለት ምን እንደሆነ ማስተማር፤
4. አላህ የፍጡሮቹን ሁሉ ማንነት የሚያውቅ በመሆኑ ማን ሊሰጠው እንደሚገባ እንደሚያውቅ፤
5. ሽርክን አውግዞ ተውሒድን ማሞገስ፤
6. ከአላህ ሌላ ያሉን አማልእክት ታቦቶች፣ ቅዱሳን ሰዎች፣ እንዲረዱት መማፀን መሰረት የሌለው መሆኑን፤
7. በዱንያ ሲመለክ የነበረ ሰው ሁሉ በዚያ ቀን አይመለከም
8. በአላህ ውሳኔ ላይ ጠንካራ እምነትን መመስረት፤
9. ቁረይሾች የጠየቁት ተአምር ለምን እንዳልተፈፀመላቸው፤
10. ነብዩ (ﷺ) ወደ በይተል መቅዲስ እና ወደ ሰማይ ያደረጉት ጉዞ ሚስጥር ምን እንደነበር መገንዘብ፤
11. የዘቁም ዛፍ በቁርአን መነሳቷን፤
12. ያለፉትን ታሪኮች እያነሱ ማስተማር ተገቢ መሆኑን፤
13. ኩራት በኢስላም የተወገዘ መሆኑን፤
14. የሰይጣንን ጠላትነት በግልፅ ማስጠንቀቅ፤
15. ሰይጣን ተከታዮቹን በንብረታቸው በልጆቻቸውና በሴቶቻቸው እንደሚገባባቸው፤
16. የዘፈን፣ የመዝሙር የዳንስ ድምፆች ዳቢሎስ ሰዎችን የሚዋጋባቸው መሳሪያዎች መሆናቸውን፤
17. አላህ የግል ባሮቹን ከሰይጣን ተንኮል እንደሚጠበቃቸው እንማራለን።

يَوۡمَ نَدۡعُواْ كُلَّ أُنَاسِۭ بِإِمَٰمِهِمۡۖ فَمَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ يَقۡرَءُونَ كِتَٰبَهُمۡ
وَلَا يُظۡلَمُونَ فَتِيلٗا ﴿٧١﴾ وَمَن كَانَ فِي هَٰذِهِۦٓ أَعۡمَىٰ فَهُوَ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ أَعۡمَىٰ وَأَضَلُّ سَبِيلٗا ﴿٧٢﴾

**71-72.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎችን ሁሉ በመሪያቸው የምንጠራበትን ቀን (አስታውስ) መጽሐፉንም በቀኙ የተሰጠ ሰው እነዚያ መጽሐፋቸውን ያነባሉ በተምር ፍሬ ስንጥቅ ላይ ያለውን ክር ያክል እንኳ አይበደሉም። በዚህች ዓለም (ልበ) እውር የሆነ ሰው እርሱ በመጨረሻይቱም ዓለም ይበልጥ እውር ነው። መንገድንም በጣም የተሳሳተ ነው።

وَإِن كَادُواْ لَيَفۡتِنُونَكَ عَنِ ٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ لِتَفۡتَرِيَ عَلَيۡنَا غَيۡرَهُۥۖ وَإِذٗا لَّٱتَّخَذُوكَ
خَلِيلٗا ﴿٧٣﴾ وَلَوۡلَآ أَن ثَبَّتۡنَٰكَ لَقَدۡ كِدتَّ تَرۡكَنُ إِلَيۡهِمۡ شَيۡـٔٗا قَلِيلًا ﴿٧٤﴾ إِذٗا لَّأَذَقۡنَٰكَ ضِعۡفَ
ٱلۡحَيَوٰةِ وَضِعۡفَ ٱلۡمَمَاتِ ثُمَّ لَا تَجِدُ لَكَ عَلَيۡنَا نَصِيرٗا ﴿٧٥﴾ وَإِن كَادُواْ لَيَسۡتَفِزُّونَكَ مِنَ
ٱلۡأَرۡضِ لِيُخۡرِجُوكَ مِنۡهَاۖ وَإِذٗا لَّا يَلۡبَثُونَ خِلَٰفَكَ إِلَّا قَلِيلٗا ﴿٧٦﴾ سُنَّةَ مَن قَدۡ أَرۡسَلۡنَا قَبۡلَكَ
مِن رُّسُلِنَاۖ وَلَا تَجِدُ لِسُنَّتِنَا تَحۡوِيلًا ﴿٧٧﴾

**73-77.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነሆ ከዚያ ወደ አንተ ካወረድነው ሌላን በእኛ ላይ ትዋሽ ዘንድ ሊፈትኑህ በእርግጥ ተቃረቡ ያን ጊዜም ወዳጅ አድርገው በያዙህ ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባላረጋጋንህም ኖሮ ወደ እነርሱ ጥቂትን ዝንባሌ ልትዘነበል በእርግጥ በተቃረብክ ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያን ጊዜ የሕይወትን ድርብ ሆነ የሞትን ድርብ እናቀምስህ ነበር። ከዚያ ላንተ በእኛ ላይ ረዳትን አታገኝም ነበር። ከምድሪቱ (ከዓረብ ምድር) ከእርሷ ያወጡህ ዘንድ ሊያሸብሩህ በእርግጥ ተቃረቡ። ያን ጊዜም ከአንተ በኋላ ጥቂትን ጊዜ እንጂ አይቆዩም ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመልዕክተኞቻችን ከአንተ በፊት በእርግጥ እንደ ላክናቸው ሰዎች ልማድ ብጤ (ይጠፉ ነበር) ለልማዳችን መለወጥን አታገኝም (አይለወጥም)።

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (73) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የሰቂፍ ልዑኮች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው «ላትን ለአንድ አመት እንድናመልክ ተወን። የእኛን ወንዝም ልክ እንደ መካ አስከብርልን» ብለው ጠየቁ። ነብዩም መልስ ከመስጠት ተቆጠቡ እነሱ ግን እየደጋገሙ ጠይቁ። «ዐረቦችን ፈርተህ ከሆነ አላህ በዚህ አዞኝ ነው በላቸው» አሏቸው። ነብዩ (ﷺ) ግን አሁንም ዝም ብለው ሳለ ዑመር ተነስተው «ነብዩ ዝም ሲሏችሁ ጥያቄያችሁን ምን ያህል እንደ ጠሉ አታውቁምን?» አሏቸው ነብዩ ግን ጥያቄያቸው ቢሳካላቸው በሚል አስበው ሳሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ኢብኑል ጀውዚ እና ዋሒዲ)

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (67-75) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የሰው ልጅ አላህ ለዋለለት ውለታ ሊያመሰግን እንደሚገባ፤
2. የሰው ልጅ የሚተገብረው ነገር ሁሉ እንደሚመዘገብበትና የትንሳኤ ቀን ሲቀርብ ደግም ከሆነ በደግ መጥፎ ከሆነ በመጥፎ እንደሚመነዳ፤
3. ይህች ያለንባት ዓለም ለሁለተኛው ዓለም የምንዘጋጅባት ዐለም መሆኗን፤
4. ትክክለኛ ሙስሊም አላህ ዘንድ ከመላኢኮች እንደሚበልጥ፤
5. አላህ ነብዩን እንደሚረዳና የእሳቸውን አስተምህሮትም በምስራቁም በምዕራቡም ይፋ እንደሚያደርገው እንማራለን።

أَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ لِدُلُوكِ ٱلشَّمۡسِ إِلَىٰ غَسَقِ ٱلَّيۡلِ وَقُرۡءَانَ ٱلۡفَجۡرِۖ إِنَّ قُرۡءَانَ ٱلۡفَجۡرِ كَانَ
مَشۡهُودٗا ٧٨ وَمِنَ ٱلَّيۡلِ فَتَهَجَّدۡ بِهِۦ نَافِلَةٗ لَّكَ عَسَىٰٓ أَن يَبۡعَثَكَ رَبُّكَ مَقَامٗا مَّحۡمُودٗا ٧٩
وَقُل رَّبِّ أَدۡخِلۡنِي مُدۡخَلَ صِدۡقٖ وَأَخۡرِجۡنِي مُخۡرَجَ صِدۡقٖ وَٱجۡعَل لِّي مِن لَّدُنكَ سُلۡطَٰنٗا
نَّصِيرٗا ٨٠ وَقُل جَآءَ ٱلۡحَقُّ وَزَهَقَ ٱلۡبَٰطِلُۚ إِنَّ ٱلۡبَٰطِلَ كَانَ زَهُوقٗا ٨١

**78-81.** ሶላትን ከፀሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ጨለማ ድረስ ስገድ የጎህንም ሶላት ስገድ የጎህ ሶላት መላዕክት የሚገኙበት ነውና።✷ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሌሊት ለአንተ ተጨማሪ የሆነችን ሶላት በቁርአን ስገድ። ጌታህ ምስጉን በሆነ ስፍራ በእርግጥ ያቆምሃል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በልም ጌታዬ ሆይ! የተወደደን ማግባት አስገባኝ የተወደደንም ማውጣት አስወጣኝ። ለእኔም ከአንተ ዘንድ የተረዳን ስልጣን አድርግልኝ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በልም እውነት መጣ ውሸትም ተወገደ እነሆ ውሸት ተወጋጅ ነውና።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አብ ሁረይራህ እንዲህ ብለዋል፡- የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ «አንድ ሰው ከሰዎች ጋር በሕብረት የሚሰግደው ሰው ግዴታ የሆነ ሶላት ብቻውን ከሚሰገደው ሶላት በሃያ አምስት እጥፍ ይበልጣል። የቀንና የሌሊት መላዕክት በፈጅር ሶላት ወቅት አንድ ላይ ይሰበሰባሉ። አቡ ሁረይራህ አያይዘውም ከፈለጋችሁ ቁርአንን አንብቡ «ሶላትን ከፀሐይ መዘንበል እስከ ሌሊት ድረስ ስገዱ። የጎህንም ሶላት ስገዱ። የጎህ ሶላት መላእከት የሚሰግዱት ነውና።» (አልኢስራእ፡ 78)

(ሀ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ኡመር እንዳስተላለፉት «በትንሳኤ ቀን ሰዎች ሁሉ በጉልበታቸው ይንበረከካሉ። ሁሉም ሕዝቦች ነብያቸውን ይከተላሉ። ማማለጃ ለነብዩ እስኪሰጥ ድረስም «እከሌ ሆይ! አማልደን ይላሉ። ያን ጊዜም አላህ ነብዩን (ﷺ) ላቅ ወዳለውና ወደ ተሞገሰው ቦታ ያነሳቸዋል።» ብለዋል።

(ለ) ጃቢር ብኑ ዐብደላህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል። «የአዛን ጥሪን የሰማና ከዚያም «አልላሁምመ ረብበል ሀዚሂድ. ደዕወቲ አትታማ ወሰ. ሰላቲ. ልቃኢማህ አቲ ሙሐመደን አል ወሲለተ ወል. ፈዲላህ ወብአስሁ አልላሁም መቃሙል. መሕሙደኒ አልለዚ ወዐድተሁ ኢነከላ ቱኽሊፉል ሚአድ» ያለ ሰው በትንሳኤ ቀን የኔ አማላጅነት ዋስትና አለው»

ከሌሊት ጉዞ (80) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- መኮች ነብዩን (ﷺ) ሊያስሩ ሲፈልጉና አላህ ደግሞ ወደ መዲና እንዲሰደዱ ሲፈልግ ነው ይህን አንቀፅ ያወረደው። (ጦበሪ እና ኢብኑ ከሲር)

وَنُنَزِّلُ مِنَ ٱلْقُرْءَانِ مَا هُوَ شِفَآءٌ وَرَحْمَةٌ لِّلْمُؤْمِنِينَ وَلَا يَزِيدُ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا خَسَارًا ﴿٨٢﴾
وَإِذَآ أَنْعَمْنَا عَلَى ٱلْإِنسَٰنِ أَعْرَضَ وَنَـَٔا بِجَانِبِهِۦ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ كَانَ يَـُٔوسًا ﴿٨٣﴾ قُلْ كُلٌّ
يَعْمَلُ عَلَىٰ شَاكِلَتِهِۦ فَرَبُّكُمْ أَعْلَمُ بِمَنْ هُوَ أَهْدَىٰ سَبِيلًا ﴿٨٤﴾

**82-84.** ከቁርኣን ለምዕመናን መድሓኒትና እዝነት የሆነን እናወርዳለን በዳዮችንም ከሳራን እንጂ ሌላ አይጨመርላቸውም። በሰው ላይ ፀጋችንን በለገስን ጊዜ ከምስጋና ይዞራል ጎኑንም ከእውነት ያርቃል። ችግርም በነካው ጊዜ ተስፋ ቆራጭ ይሆናል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁሉም በሚመስለው መንገድ ላይ ይሠራል። ጌታችሁም እርሱ መንገዱ ቀጥተኛ የሆነውን ሰው አዋቂ ነው በላቸው።

وَيَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلرُّوحِ ۖ قُلِ ٱلرُّوحُ مِنْ أَمْرِ رَبِّى وَمَآ أُوتِيتُم مِّنَ ٱلْعِلْمِ إِلَّا قَلِيلًا ﴿٨٥﴾

**85.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሩህ ይጠይቁሃል ሩህ ከጌታዬ ነገር ነው። ከእውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም በላቸው።

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (85) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አይሁዶች እራሳቸው ወይም በመኮች አማካኝነት ስለ ሩህ ጠይቀዋቸው ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው (ዋሂዲና ኢብኑ ከሲር)

وَلَئِن شِئْنَا لَنَذْهَبَنَّ بِٱلَّذِىٓ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ ثُمَّ لَا تَجِدُ لَكَ بِهِۦ عَلَيْنَا وَكِيلًا ﴿٨٦﴾
إِلَّا رَحْمَةً مِّن رَّبِّكَ ۚ إِنَّ فَضْلَهُۥ كَانَ عَلَيْكَ كَبِيرًا ﴿٨٧﴾

**86-87.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ብንሻ ያንን ወደ አንተ ያወረድነውን በእርግጥ እንወስድብሃለን። ከዚያ ለአንተ በእኛ ላይ በእርሱ ለማስመለስ ተያዢን አታገኝም። ግን ከጌታህ በሆነው እዝነት ጠበቅነው ችሮታው አንተ ላይ ታላቅ ነውና።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፉ ከአንቀፅ (76-86) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አምስት አውቃት ሶላቶችን ጊዜያቸውን ጠብቆ መስገዱ አስፈላጊ መሆኑን፤
2. የሌሊት ሶላት በነብዩ (ﷺ) ላይ ግዴታ መሆኑንና ለሙስሊሞች ግን ሱና መሆኑን የኢስላም መመሪያ ገር መሆኑን፤
3. ማንኛውም የተፈቀደ ስራ ሲጀምሩና ሲጨርሱ ወደ አላህ ዱዓ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን፤
4. አላህ እውነትን እውነተኞች እስከተንቀሳቀሱ ድረስ እንደሚረዳ ውሸትን ደግሞ እድሜው ቢረዝምም ማክሰሙ እንደማይቀር፤
5. ትምህርትን ለመማር መተናነስና ባወቁት ነገር መታለል አስፈላጊ እንዳልሆነ እና እውቀት በየጊዜው የሚጨምር እድገቱ የማያበቃ በመሆኑ የሚጠቅም የሚጠቅመውን ነገር ብቻ መማር አስፈላጊ መሆኑን እንማራለን።

قُل لَّئِنِ ٱجۡتَمَعَتِ ٱلۡإِنسُ وَٱلۡجِنُّ عَلَىٰٓ أَن يَأۡتُواْ بِمِثۡلِ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ لَا يَأۡتُونَ بِمِثۡلِهِۦ وَلَوۡ
كَانَ بَعۡضُهُمۡ لِبَعۡضٖ ظَهِيرٗا ٨٨ وَلَقَدۡ صَرَّفۡنَا لِلنَّاسِ فِي هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ مِن كُلِّ مَثَلٖ فَأَبَىٰٓ
أَكۡثَرُ ٱلنَّاسِ إِلَّا كُفُورٗا ٨٩

88-89. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎችና ጋኔኖች የዚህን ቁርኣን ቢጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆኑም እንኳ ብጤውን አያመጡም በላቸው። በዚህም ቁርኣን ውስጥ ከምሳሌው ሁሉ ለሰዎች በእርግጥ መላልሰን (አብራራን) አብዛኞቹም ሰዎች ክህደትን እንጂ ሌላን እምቢ አሉ።

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (88) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰላም ኢብኑ ሚሽከም የተባለ አይሁድ ጓደኞቹን ይዞ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ «የእኛን ቂብላ ትተህ አስተምህሮትህ ከኦሪት አስተምህሮት ጋር የማይስማማ ሆኖ እንዴት ነው የምንከተለህ» በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪና ዋሒዲ)

وَقَالُواْ لَن نُّؤۡمِنَ لَكَ حَتَّىٰ تَفۡجُرَ لَنَا مِنَ ٱلۡأَرۡضِ يَنۢبُوعًا ٩٠ أَوۡ تَكُونَ لَكَ جَنَّةٞ مِّن نَّخِيلٖ
وَعِنَبٖ فَتُفَجِّرَ ٱلۡأَنۡهَٰرَ خِلَٰلَهَا تَفۡجِيرًا ٩١ أَوۡ تُسۡقِطَ ٱلسَّمَآءَ كَمَا زَعَمۡتَ عَلَيۡنَا كِسَفًا
أَوۡ تَأۡتِيَ بِٱللَّهِ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ قَبِيلًا ٩٢ أَوۡ يَكُونَ لَكَ بَيۡتٞ مِّن زُخۡرُفٍ أَوۡ تَرۡقَىٰ فِي ٱلسَّمَآءِ وَلَن
نُّؤۡمِنَ لِرُقِيِّكَ حَتَّىٰ تُنَزِّلَ عَلَيۡنَا كِتَٰبٗا نَّقۡرَؤُهُۥۗ قُلۡ سُبۡحَانَ رَبِّي هَلۡ كُنتُ إِلَّا بَشَرٗا رَّسُولٗا ٩٣

90-93. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አሉም ለእኛ ከምድር ምንጭን እስከምታፈልቅልን ድረስ ለአንተ አናምንም። ወይም ከዘንባባዎችና ከወይን የሆነች አትክልት ለአንተ እስከምትኖርህና በመካከሏም ጅረቶችን በብዛት እስከምታንቧቧ። ወይም እንደምትለው ከሰማይ ቁራጮችን በእኛ ላይ እስከምታወርድ ወይም አላህንና መላዕክትን በግልጽ እስከምታመጣ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወይም ከወርቅ የሆነ ቤት ለአንተ እስከሚኖርህ ወይም በሰማይ እስከምትወጣ፤ ለመውጣትህም በእኛ ላይ የምናነበው የሆነን መጽሐፍ እስከምታወርድልን ድረስ ፈጽሞ አናምንልህም አሉ። ጌታዬ ጥራት ይገባው። እኔ ሰውና መልዕክተኛ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው።

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ (90) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ መሪዎች ተሰባስበው ሙሐመድን (ﷺ) አናግሩት አስጨርሱት በማለት ከተመካከሩ በኋላ የተወሰኑ ሰዎችን ልከው «ዘመዶችህ ሊያናግሩህ ይፈልጉሃል» በማለት ላኩባቸው። ነብዩም (ﷺ) «በፍጥነት መጡላቸውና ...» (ጦበሪ እና ዋሒዲ)

وَمَا مَنَعَ ٱلنَّاسَ أَن يُؤْمِنُوٓاْ إِذْ جَآءَهُمُ ٱلْهُدَىٰٓ إِلَّآ أَن قَالُوٓاْ أَبَعَثَ ٱللَّهُ بَشَرًا رَّسُولًا ﴿٩٤﴾ قُل
لَّوْ كَانَ فِى ٱلْأَرْضِ مَلَٰٓئِكَةٌ يَمْشُونَ مُطْمَئِنِّينَ لَنَزَّلْنَا عَلَيْهِم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ مَلَكًا رَّسُولًا ﴿٩٥﴾
قُلْ كَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدًۢا بَيْنِى وَبَيْنَكُمْ ۚ إِنَّهُۥ كَانَ بِعِبَادِهِۦ خَبِيرًۢا بَصِيرًا ﴿٩٦﴾

**94-96.** ሰዎችን መሪ ቁርኣን በመጣላቸው ጊዜ በሱ ከማመን አላህ ሰውን መልዕክተኛ አድርጎ ላከን? ማለታቸው ብቻ እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ላይ ተረጋግተው የሚጓዙ መላእክት ቢኖሩ ኑሮ ከሰማይ የመልአክ መልዕክተኛ እናወርድላቸው ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእኔና በእናንተ መካከል ላለን ልዩነት መስካሪ በአላህ በቃ። ምክኒያቱም እርሱ ባሮቹን ጠንቅቆ አዋቂና ተመልካች ነውና በላቸው።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (87-96) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ቁርኣን በተለያዩ ዘርፎቹ አሸናፊና የበላይነቱን ማመን፤
2. ጋኔኖችም ሆኑ ሰዎች የቁርኣንን መሰል ማምጣት ሳይችሉ መቅረታቸው የአላህ ቃል እንጂ የሰው ቃል መሆኑን እንደሚያረጋግጥ፤
3. ከሓዲያን ነብዩ (ﷺ) የተለያዩ ተዐምሮችን እንዲያሳዩዋቸው ቢጠይቋቸው አላህ እንዳልተቀበላቸው።

وَمَن يَهْدِ ٱللَّهُ فَهُوَ ٱلْمُهْتَدِ ۖ وَمَن يُضْلِلْ فَلَن تَجِدَ لَهُمْ أَوْلِيَآءَ مِن دُونِهِۦ ۖ وَنَحْشُرُهُمْ يَوْمَ
ٱلْقِيَٰمَةِ عَلَىٰ وُجُوهِهِمْ عُمْيًا وَبُكْمًا وَصُمًّا ۖ مَّأْوَىٰهُمْ جَهَنَّمُ ۖ كُلَّمَا خَبَتْ زِدْنَٰهُمْ سَعِيرًا ﴿٩٧﴾
ذَٰلِكَ جَزَآؤُهُم بِأَنَّهُمْ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَقَالُوٓاْ أَءِذَا كُنَّا عِظَٰمًا وَرُفَٰتًا أَءِنَّا لَمَبْعُوثُونَ خَلْقًا
جَدِيدًا ﴿٩٨﴾ ۞ أَوَلَمْ يَرَوْاْ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ قَادِرٌ عَلَىٰٓ أَن يَخْلُقَ مِثْلَهُمْ
وَجَعَلَ لَهُمْ أَجَلًا لَّا رَيْبَ فِيهِ فَأَبَى ٱلظَّٰلِمُونَ إِلَّا كُفُورًا ﴿٩٩﴾

**97-99.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ያቀናው ሰው በእርግጥም የተቀና ማለት እርሱ ብቻ ነው። እርሱ ያጠመማቸውን ሰዎች ግን ከቅጣቱ የሚያድናቸው ማንም ወዳጅ አታገኝላቸውም። የትንሳኤ ቀንም እውር፤ ዲዳና፤ ደንቆሮ አድርገን በፊቶቻቸው* እንሰበስባቸዋለን። መኖሪያቸውም ገሀነም ናት። ሀይሏ በደከመ ጊዜም ግለትን እንጨምርላቸዋለን። ይህ የሚጠብቃቸው ቅጣታቸው ነው። ምክንያቱም በአንቀጾቻችን ክደው የበሰበሰ አጥንት ከሆንና (ወደ አፈራነት) ከተቀየርን በኋላ እንደ አዲስ ፍጥረት ሆነን እንቀሰቀሳለን? ብለዋልና። ያ ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ አላህ

ብጤያቸውን በመፍጠር ላይ ቻይ መሆኑን በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበትንም ጊዜ ለሞትም ለትንሳኤም ለእነርሱ የወሰነ መሆኑን አላወቁምን? በደለኞችም ከክህደት በቀር እምቢ አሉ።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት አንድ ሰው «የአላህ ነብይ ሆይ! በትንሳኤ ቀን ከሓዲያንን በፊታቸው እንዲሄዱ ከሞት ይቀሰቅሳቸዋልን?» ሲል ጠየቀ። እሳቸውም «በሁለት እግሮቹ በምድር ላይ እንዲሄድ ያደረገው እሱ ሆኖ ሳለ በትንሳኤ ቀን በፊቱ ላይ ተደፍቶ እንዲሄድ ለማድረግ አይችልምን?» አሉት አቡ ቀታዳህ የተባሉት ሌላው የሐዲሱ አስተላላፊ በዚህ ሐዲስ ላይ የሚከተለውን ጨምረዋል «እንዴታ! በጌታችን ክብር ይሁንብን!»

قُل لَّوۡ أَنتُمۡ تَمۡلِكُونَ خَزَآئِنَ رَحۡمَةِ رَبِّيٓ إِذٗا لَّأَمۡسَكۡتُمۡ خَشۡيَةَ ٱلۡإِنفَاقِۚ وَكَانَ ٱلۡإِنسَٰنُ قَتُورٗا ١٠٠

**100.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ የጌታዬን የችሮታ መካዚኖች ብትይዙ ኖሮ ያን ጊዜ በማውጣታችሁ ማለቋን በመፍራት በጨበጣችሁ ነበር። ሰው በጣም ቆጣቢ ነውና።

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَىٰ تِسۡعَ ءَايَٰتِۭ بَيِّنَٰتٖۖ فَسۡـَٔلۡ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ إِذۡ جَآءَهُمۡ فَقَالَ لَهُۥ فِرۡعَوۡنُ
إِنِّي لَأَظُنُّكَ يَٰمُوسَىٰ مَسۡحُورٗا ١٠١ قَالَ لَقَدۡ عَلِمۡتَ مَآ أَنزَلَ هَٰٓؤُلَآءِ إِلَّا رَبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلۡأَرۡضِ بَصَآئِرَ وَإِنِّي لَأَظُنُّكَ يَٰفِرۡعَوۡنُ مَثۡبُورٗا ١٠٢ فَأَرَادَ أَن يَسۡتَفِزَّهُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ
فَأَغۡرَقۡنَٰهُ وَمَن مَّعَهُۥ جَمِيعٗا ١٠٣

**101-103.** ለሙሳ ግልጽ የሆኑን ዘጠኝ ተዐምራቶች በእርግጥ ሰጠነው። በመጣቸውም ጊዜ የኢስራኤልን ልጆች ከፈርኦን እንዲለቀቁ ጠይቅ አልነው ፈርኦንም፡- ሙሳ ሆይ እኔ የተደገመብህ መሆንህን በእርግጥ እጠረጥርሀለሁ አለው። ሙሳም፡- (ፈርዖውን ሆይ!) እነዚህን ተዐምራቶች መግለጫዎች ሲሆኑ የሰማያትና የምድር ጌታ እንጂ ሌላ እንዳላወረዳቸው በእርግጥ አውቀሀል። እኔም ፈርዖን ሆይ፣ የምትጠፋ መሆንህን በእርግጥ እጠረጥርሀለሁ አለው። ከምድርም ሊያባርራቸው አሰበ። እርሱንና ከእርሱ ጋር የነበሩትን ሰዎች ሁሉንም አሰመጥናቸው።

وَقُلۡنَا مِنۢ بَعۡدِهِۦ لِبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱسۡكُنُواْ ٱلۡأَرۡضَ فَإِذَا جَآءَ وَعۡدُ ٱلۡأٓخِرَةِ جِئۡنَا بِكُمۡ لَفِيفٗا ١٠٤

**104.** ከእርሱም በኋላ ለኢስራኤል ልጆች ምድሪቱን ተቀመጡባት የኋለኛይቱም ሰዓት ቀጠሮ በመጣ ጊዜ እናንተን የተከማቻችሁ ስትሆኑ እናመጣችኋለን አልናቸው።

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (97-104) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የከሃዲያ ቅጣት የቱን ያህል ሊከብድ እንደሚችል፤
2. አላህ ማስገኘትና ህያው ማድረግ እንደሚችልና ከሞቱ በኋላ መቀስቀስ እንደሚችል፤
3. ልዩ ልዩ ተዐምራትን ማየት ለከሃዲ ልቦና ምንም ፋይዳ የሌለው መሆኑን እንማራለን፡፡

وَبِٱلْحَقِّ أَنزَلْنَٰهُ وَبِٱلْحَقِّ نَزَلَ ۗ وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا مُبَشِّرًا وَنَذِيرًا ﴿١٠٥﴾ وَقُرْءَانًا فَرَقْنَٰهُ لِتَقْرَأَهُۥ
عَلَى ٱلنَّاسِ عَلَىٰ مُكْثٍ وَنَزَّلْنَٰهُ تَنزِيلًا ﴿١٠٦﴾ قُلْ ءَامِنُوا۟ بِهِۦٓ أَوْ لَا تُؤْمِنُوٓا۟ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟
ٱلْعِلْمَ مِن قَبْلِهِۦٓ إِذَا يُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ يَخِرُّونَ لِلْأَذْقَانِ سُجَّدًا ﴿١٠٧﴾ وَيَقُولُونَ سُبْحَٰنَ رَبِّنَآ إِن
كَانَ وَعْدُ رَبِّنَا لَمَفْعُولًا ﴿١٠٨﴾ وَيَخِرُّونَ لِلْأَذْقَانِ يَبْكُونَ وَيَزِيدُهُمْ خُشُوعًا ۩ ﴿١٠٩﴾

**105-109.** ቁርኣንን በእውነትም አወረድነው፡፡ በእውነትም ወረደ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተንም አብሳሪና አስፈሪ አድርገን እንጂ አልላክንህም፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቁርኣንን በሰዎች ላይ በዝግታ ላይ ሆነህ ታነበው ዘንድ ከፋፈልነው፡፡ ቀስ በቀስ ማውረድንም አወረድነው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርሱ እመኑ ወይም አትመኑ በላቸው፡፡ እነዚያ ከእርሱ በፊት እውቀትን የተሰጡት በእነርሱ ላይ በተነበበ ጊዜ ሰጋጆች ሆነው በሸንጎበቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ፡፡ ጌታችን ጥራት ይገባው፡፡ እነሆ የጌታችን ተስፋ ተፈጻሚ ነው ይላሉ፡፡ እያለቀሱም በሸንጎበቶቻቸው ላይ ይወድቃሉ፡፡ ፍርሃትንም ይጨምርላቸዋል፡፡

قُلِ ٱدْعُوا۟ ٱللَّهَ أَوِ ٱدْعُوا۟ ٱلرَّحْمَٰنَ ۖ أَيًّا مَّا تَدْعُوا۟ فَلَهُ ٱلْأَسْمَآءُ ٱلْحُسْنَىٰ ۚ وَلَا تَجْهَرْ بِصَلَاتِكَ
وَلَا تُخَافِتْ بِهَا وَٱبْتَغِ بَيْنَ ذَٰلِكَ سَبِيلًا ﴿١١٠﴾ وَقُلِ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ٱلَّذِى لَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ
يَكُن لَّهُۥ شَرِيكٌ فِى ٱلْمُلْكِ وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ وَلِىٌّ مِّنَ ٱلذُّلِّ ۖ وَكَبِّرْهُ تَكْبِيرًۢا ﴿١١١﴾

**110-111.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህን ጥሩ ወይም አልረህማንን ጥሩ፡፡ ከሁለቱ ማንኛውንም ስም ብትጠሩ መልካም ነው፡፡ ለእርሱ ብዙ መልካም ስሞች* አሉትና በላቸው፡፡ በስግደትህ ስታነብ በጣም በድምጽህ አትጬህ፡፡ በእርሷም በጣም ድምጽህን ዝቅ አታድርግ፡፡ በሁለቱ መካከል የሆነ መንገድን ፈልግ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምስጋና ሁሉ ለዚያ ልጅን ላልያዘው ለእርሱም በንግስናው ተጋሪ ለሌለው ለእርሱም ከውርደት የሚያድነው ወዳጅ ለሌለው ለአላህ ብቻ ይገባው በል፡፡ እርሱን ማክበርንም አክብረው፡፡

✷ አላህ አያሌ መልካም ስሞች አሉት። በሰፊው በአል አዕራፍ. (180) ኛው አንቀፅ ግርጌ ላይ አልፏል።

ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ምዕራፉ (110) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:. አንድ ቀን ነብዩ (ﷺ) በመካ ውስጥ እየሰገዱ «ያረህማኑ ያረሂሙ» እያሉ አላህን ሲለምኑ የሰሙ ከሓዲያን «ሙሐመድ አንድ አምላክ ነበር የሚገዛው ዛሬ ግን ሁለት አምላክ መገዛት ጀመረ። አላህና ረህማን። እኛ የምናውቀው የየማማውን ረህማን ብቻ ነው» በማለታቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ጦበሪ)

**ከሌሊት ጉዞ ምዕራፍ ከአንቀፅ (105-111) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የሰዎችን ጥያቄ እንደአስፈላጊነቱ ሊፈታ ቁርኣን በ (23) ዓመት ውስጥ ተከፋፍሎ እንደወረደ፤
2. አላህ ብዙ ውብና መልካም ስሞች ስላሉት በእነሱ እንድንለምነውና ከእሱ ሌላ ማንንም መለመን እንደሌለኢብኑ፤
3. አላህ ልጅ፤ አጋር፤ ረዳት እንደሌለው በትክክል ማመን፤ አላህን ማመስገን፤ ማወደስ፤ ማላቅ ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የሌሊት ጉዞ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (18)
# የዋሻው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልከህፍ)

سُورَةُ الكَهۡفِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (110) ናቸው።
### የሱረቱ አል ከህፍ መግቢያ

በዚህ ስም የሰየሙት ራሳቸው ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ናቸው። ሙስሊምና አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ «ከአል-ከህፍ ምእራፍ የመጀመሪያዎቹን አስር አንቀፆች በቃሉ የሐፈዘ ሰው ከደጃል ፊትና ይጠበቃል» ብለዋል።

ኢብኑ መርደወይህ በዘገቡት ሐዲስ « የዋሻው ህዝቦች ምእራፍ» ብለው መሰየማቸው ተዘግቧል።

ከመቶ በላይ የሆነ አንቀፆችን የያዘ ሲሆን በመጀመሪያ ቁርኣንን በማውረዱ አላህ ሊመሰገን እንደሚገባውና የቁርኣን ዋና ተልኮው በመልካም ማብሰርና ከመጥፎ ስራ ማስፈራራት እንደሆነ፤ ለአላህ ልጅ አለው የሚሉትን የአጋሪ ቡድኖች አስፈራርቶ ነብዩ ሙሐመድ ከሓዲያን እንዲሰልሙ ከፍተኛ ጉጉት እንደነበራቸው ይገልፃል።

ከዚያም በማስከተል የዋሻ ሰዎች ታሪክን በዝርዝር አስቀምጦ የእነሱን ታሪክ ለአላህ ሃያልነትና ለሞቶ መነሳት እውነትነት ትልቅ ማስረጃ መሆኑን ያሳያል።

ከዚያም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቁርኣን እንዲቀሩና በእሱም ከሓዲያንን እንዲያስፈራሩ፤ አማኝን እንዲያበስሩ ያዘዛቸው። የሁለት ሰዎችን ማለትም አንዱ በገንዘቡ ሁለተኛው ለአላህ ሲል የሚሞቱን ሰዎች ታሪክ በምሳሌነት ጠቅሶ አስተምሯል። ነብዩ ሙሳ ከነብዩ ኸድር ጋር ያሳለፏቸውን አስገራሚ ታሪኮች በዝርዝር አውስቶ የዙል ቀርነይን ታሪክ ቀንጨብ በማድረግ ካነሳ በኋላ የቂያማን ቀንና በውስጧ የሚከሰቱትን ነገሮች፤ የአማኞችን ምንዳ፤ የአላህን የተሟላ እውቀት በማስተማር ትምህርቱን ያጠናቅቃል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِيٓ أَنزَلَ عَلَىٰ عَبۡدِهِ ٱلۡكِتَٰبَ وَلَمۡ يَجۡعَل لَّهُۥ عِوَجَاۜ ١ قَيِّمٗا لِّيُنذِرَ بَأۡسٗا
شَدِيدٗا مِّن لَّدُنۡهُ وَيُبَشِّرَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٱلَّذِينَ يَعۡمَلُونَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أَنَّ لَهُمۡ أَجۡرًا حَسَنٗا ٢
مَّٰكِثِينَ فِيهِ أَبَدٗا ٣ وَيُنذِرَ ٱلَّذِينَ قَالُواْ ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ وَلَدٗا ٤ مَّا لَهُم بِهِۦ مِنۡ عِلۡمٖ
وَلَا لِأٓبَآئِهِمۡۚ كَبُرَتۡ كَلِمَةٗ تَخۡرُجُ مِنۡ أَفۡوَٰهِهِمۡۚ إِن يَقُولُونَ إِلَّا كَذِبٗا ٥

**1-5.** ምስጋና ሁሉ ለዚያ መጽሐፉን በውስጡ ቅንጣት መጣመምን* ሳያደርግ በባሪያው (በሙሐመድ) ላይ ላወረደው ለአላህ ብቻ ይገባው። ቀጥተኛ ሲሆን ከራሱ ዘንድ የሆነን ብርቱን ቅጣት ሊያስፈራራበት እነዚያንም በጎ ሰሪዎችን ለእነርሱ መልካም ምንዳ ያላቸው መሆኑንና በእርሱ ውስጥ ዘለዓለም የሚቆዩበት ሊያበስርበት አወረድነው። እነዚያንም አላህ ልጅን ይዟል ያሉትን ሊያስፈራራበት ቁርኣንን አወረደው። ለእነርሱም ሆነ ለአባቶቻቸው ስለ አላህ ልጅ መኖር ምንም እውቀት የላቸውም። ከአፎቻቸው የሚወጣው ቃል ምን አከበደው፣ ውሸትን እንጂ ሌላን አይናገሩም።

* «ይህ አንቀፅ፤ (ቁርኣንን) አያስተነትኑምን? ከአላህ ሌላ...» (አንኒሳእ፡ 82) እና «በእነዚህ «ቁርኣን ውስጥ ሰዎች ይገሠጹ ዘንድ ከየምሳሌው .» (አዝዙመር፡ 27-28) ያሉት የቁርኣን አናቅፅ ሁሉ ቁርኣን በመሀሉ አንድም ስህተትና ግጭት እንደሌለው የሚያመለክቱ ግልፅ ማስረጃዎች ናቸው።

ከዋሻው ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ይህ አንቀፅ የወረደው መኮች ነድር ቢን ሐሪስ፤ ዑቅባህ ቢን አቡ ሙዓይጥ ወደ መዲና አይሁድ ልከው የነብዩን (ﷺ) ባህሪ እንዲጠይቁ አድርገው ነበርና አይሁዶቹም ስለ ሶስት ነገሮች ጠየቁ። ነገ እነግራችኋላሁ ብለዋቸው ተመለሱ። ኢንሻ አላህ ሳይሉ የተባለው ነገር መልሱ ሳይገኝ አስራ አምስት ቀን ሞላው። መኮች ነድር ቢን ሐሪስንና ዑቅባህ ቢን አቢሙአይጥ አይሁድ ሙህራንን ስለ ነብዩ እንዲጠይቁ ልከዋቸው ሲጠይቋቸው ከሶስት ነገሮች ጠይቁትና በትክክል ከነገራችሁ እውነትም መልዕክተኛው ነው። ይህን ካልነገራችሁ ግን ቀጣፊ ነው።

1. ኛ ስለ እነዚያ አስገራሚ ወጣቶች ታሪክ
2. ኛ ስለዚያ ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ያዳረሰ ሰው ታሪክ
3. ኛ ስለ ሩህ ጠይቁት አሏቸውና ሲጠይቋቸው አላህ ከፈቀደ ሳይሉ ነገ እንግራችኋለሁኝ ብለው ሳሉ እስከ አስራ አምስት ቀን ስለቆዩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ)

فَلَعَلَّكَ بَٰخِعٞ نَّفۡسَكَ عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِمۡ إِن لَّمۡ يُؤۡمِنُواْ بِهَٰذَا ٱلۡحَدِيثِ أَسَفًا ٦ إِنَّا جَعَلۡنَا مَا عَلَى
ٱلۡأَرۡضِ زِينَةٗ لَّهَا لِنَبۡلُوَهُمۡ أَيُّهُمۡ أَحۡسَنُ عَمَلٗا ٧ وَإِنَّا لَجَٰعِلُونَ مَا عَلَيۡهَا صَعِيدٗا جُرُزًا ٨

**6-8.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዚህ ንግግር በቁርኣን ካላመኑ በፈለጎቻቸው ላይ በቁጭት ነፍስህን አጥፊ ልትሆን ይፈራልሀል። እኛ ማንኛቸው ሥራው ያማረ መሆኑን ልንፈትናቸው በምድር ላይ ያለን ሁሉ የእርሷ ጌጥ አደረግነው። እኛ በእርሷ ላይ ያለውን ሁሉ ወስደን በመጨረሻ በእርግጥ ቡቃያ የሌለበት ምልጥ አፈር አድራጊዎች ነን።

أَمْ حَسِبْتَ أَنَّ أَصْحَٰبَ ٱلْكَهْفِ وَٱلرَّقِيمِ كَانُوا۟ مِنْ ءَايَٰتِنَا عَجَبًا ﴿٩﴾ إِذْ أَوَى ٱلْفِتْيَةُ إِلَى ٱلْكَهْفِ فَقَالُوا۟ رَبَّنَآ ءَاتِنَا مِن لَّدُنكَ رَحْمَةً وَهَيِّئْ لَنَا مِنْ أَمْرِنَا رَشَدًا ﴿١٠﴾ فَضَرَبْنَا عَلَىٰٓ ءَاذَانِهِمْ فِى ٱلْكَهْفِ سِنِينَ عَدَدًا ﴿١١﴾ ثُمَّ بَعَثْنَٰهُمْ لِنَعْلَمَ أَىُّ ٱلْحِزْبَيْنِ أَحْصَىٰ لِمَا لَبِثُوٓا۟ أَمَدًا ﴿١٢﴾

**9-12.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዋሻውና የሰሌዳው ባለቤቶች ከተዐምራቶቻችን ሲሆኑ ግሩም መሆናቸውን አሰብክን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወጣቶቹ ወደ ዋሻው በተጠጉና ጌታችን ሆይ፣ ከአንተ ዘንድ እዝነትን ስጠን ለእኛም ከነገራችን ቅንን ነገር አዘጋጅልን ባሉ ጊዜ የሆነውን ታሪክ (አስታውስ)። በዋሻውም ውስጥ የተቆጠሩን ዓመታት በጆሮዎቻቸው ላይ መታንባቸው። ከዚያ ከሁለቱ ክፍሎች ለቆዩት ጊዜ ልክ ያረጋገጠው ማንኛው መሆኑን ልናውቅ ከተኙበት አስነሳናቸው።

نَّحْنُ نَقُصُّ عَلَيْكَ نَبَأَهُم بِٱلْحَقِّ ۚ إِنَّهُمْ فِتْيَةٌ ءَامَنُوا۟ بِرَبِّهِمْ وَزِدْنَٰهُمْ هُدًى ﴿١٣﴾ وَرَبَطْنَا عَلَىٰ قُلُوبِهِمْ إِذْ قَامُوا۟ فَقَالُوا۟ رَبُّنَا رَبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ لَن نَّدْعُوَا۟ مِن دُونِهِۦٓ إِلَٰهًا ۖ لَّقَدْ قُلْنَآ إِذًا شَطَطًا ﴿١٤﴾ هَٰٓؤُلَآءِ قَوْمُنَا ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةً ۖ لَّوْلَا يَأْتُونَ عَلَيْهِم بِسُلْطَٰنٍۭ بَيِّنٍ ۖ فَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا ﴿١٥﴾ وَإِذِ ٱعْتَزَلْتُمُوهُمْ وَمَا يَعْبُدُونَ إِلَّا ٱللَّهَ فَأْوُۥٓا۟ إِلَى ٱلْكَهْفِ يَنشُرْ لَكُمْ رَبُّكُم مِّن رَّحْمَتِهِۦ وَيُهَيِّئْ لَكُم مِّنْ أَمْرِكُم مِّرْفَقًا ﴿١٦﴾

**13-16.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ወሬያቸውን በአንተ ላይ በእውነት እንተርካለን። እነርሱ በጌታቸው በትክክል ያመኑ ወጣቶች ናቸው። ወደ ቀናው መንገድ መመራትንም ጨመርንላቸው። በንጉሳቸው ፊት በቆሙና ጌታችን የሰማያትና የምድር ጌታ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክን አንገዛም። ከእሱ ሌላን ብናመልክ ወሰን ያለፈን ንግግር በእርግጥ ተናገርን ባሉ ጊዜ ልቦቻቸውን በእምነት እርስ በራሳቸው አጠነከርን። እነዚህ ህዝቦቻችን ከእርሱ ሌላ አማልክትን ያዙ። እውነተኞች ከሆኑ በእነርሱ ላይ ግልጽ ማስረጃን ለምን አያመጡም። በአላህ ላይ ውሸትን ከሚቀጣጥፍ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን

ነው? አሉ። እነርሱንና ያንን ከአላህ ሌላ የሚገዙትን በተለያችሁ ጊዜ ወደ ዋሻው ተጠጉ። ጌታችሁ ለእናንተ ከችሮታው ይዘረጋላችኋልና ከነገራችሁም ለእናንተ መጠቃቀሚያ ያዘጋጅላችኋል (ተባባሉ)።

۞ وَتَرَى ٱلشَّمْسَ إِذَا طَلَعَت تَّزَٰوَرُ عَن كَهْفِهِمْ ذَاتَ ٱلْيَمِينِ وَإِذَا غَرَبَت تَّقْرِضُهُمْ ذَاتَ ٱلشِّمَالِ
وَهُمْ فِى فَجْوَةٍ مِّنْهُ ۚ ذَٰلِكَ مِنْ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ ۗ مَن يَهْدِ ٱللَّهُ فَهُوَ ٱلْمُهْتَدِ ۖ وَمَن يُضْلِلْ فَلَن تَجِدَ لَهُۥ وَلِيًّا
مُّرْشِدًا ﴿١٧﴾ وَتَحْسَبُهُمْ أَيْقَاظًا وَهُمْ رُقُودٌ ۚ وَنُقَلِّبُهُمْ ذَاتَ ٱلْيَمِينِ وَذَاتَ ٱلشِّمَالِ ۖ وَكَلْبُهُم بَٰسِطٌ
ذِرَاعَيْهِ بِٱلْوَصِيدِ ۚ لَوِ ٱطَّلَعْتَ عَلَيْهِمْ لَوَلَّيْتَ مِنْهُمْ فِرَارًا وَلَمُلِئْتَ مِنْهُمْ رُعْبًا ﴿١٨﴾

**17-18.** ተመልካች ሆይ፣ ፀሐይዋ በወጣች ጊዜ ከዋሻቸው ወደ ቀኝ ጎን ስታዘነብል ታያታለህ። በገባችም ጊዜ ከሰፊው ዋሻ ውስጥ እያሉ በግራ በኩል ትተዋቸዋለች። ይህ ከአላህ ተዐምራት አንዱ ነው። አላህ ያቀናው ሰው በእርግጥም የተቀናው እርሱ ብቻ ነው። እርሱ ያጠመመውን ሰው ደግሞ ቅኑን መንገድ የሚመራው ረዳት ማንንም አታገኝለትም። (ተመልካች ሆይ!) እነርሱ በጥልቅ እንቅልፍ ውስጥ እያሉ የነቁ ይመስሉሃል። ወደቀኝና ወደ ግራ ጎናቸው እናገላብጣቸዋለን። ውሻቸውም በዋሻቸው በር ላይ የፊት እግሩን ዘርግቷል። በእነርሱ ላይ ብታያቸው ኖሮ ከእነርሱ በሸሸህና በፍርሀት በተሞላህ ነበር።

وَكَذَٰلِكَ بَعَثْنَٰهُمْ لِيَتَسَآءَلُوا۟ بَيْنَهُمْ ۚ قَالَ قَآئِلٌ مِّنْهُمْ كَمْ لَبِثْتُمْ ۖ قَالُوا۟ لَبِثْنَا يَوْمًا أَوْ بَعْضَ
يَوْمٍ ۚ قَالُوا۟ رَبُّكُمْ أَعْلَمُ بِمَا لَبِثْتُمْ فَٱبْعَثُوٓا۟ أَحَدَكُم بِوَرِقِكُمْ هَٰذِهِۦٓ إِلَى ٱلْمَدِينَةِ فَلْيَنظُرْ
أَيُّهَآ أَزْكَىٰ طَعَامًا فَلْيَأْتِكُم بِرِزْقٍ مِّنْهُ وَلْيَتَلَطَّفْ وَلَا يُشْعِرَنَّ بِكُمْ أَحَدًا ﴿١٩﴾ إِنَّهُمْ إِن
يَظْهَرُوا۟ عَلَيْكُمْ يَرْجُمُوكُمْ أَوْ يُعِيدُوكُمْ فِى مِلَّتِهِمْ وَلَن تُفْلِحُوٓا۟ إِذًا أَبَدًا ﴿٢٠﴾

**19-20.** እንዳስተኛናቸው ሁሉ በመካከላቸው እንዲጠያየቁ ቀሰቀስናቸው። ከእነርሱ አንድ ተናጋሪ ምን ያህል ቆያችሁ አለ? ሌሎች አንድን ቀን ወይም የቀንን ከፊል ቆየን አሉ። ጌታችሁ የቆያችሁትን ጊዜ ልክ አዋቂ ነው። ከዚህም ገንዘባችሁ ጋር አንዳችሁን ወደ ከተማይቱ ላኩ። ከምግብ የትኛዋ ንፁህ መሆኗንም ይመልከት። ከእነርሱም (ከንፁሑ) ምግብን ያምጣላችሁ። ቀስም ይበል። በእናንተም አንድንም ሰው አያሳውቅ እነርሱ በእናንተ ላይ ቢዘልቁ ይቀጠቅጧችኋል። ወይም ወደ ሃይማኖታቸው ይመልሷችኋል ያን ጊዜ በፍፁም ፍላጎታችሁን አታገኙም (ተባባሉ)።

وَكَذَٰلِكَ أَعۡثَرۡنَا عَلَيۡهِمۡ لِيَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞ وَأَنَّ ٱلسَّاعَةَ لَا رَيۡبَ فِيهَآ
إِذۡ يَتَنَٰزَعُونَ بَيۡنَهُمۡ أَمۡرَهُمۡۖ فَقَالُواْ ٱبۡنُواْ عَلَيۡهِم بُنۡيَٰنٗاۖ رَّبُّهُمۡ أَعۡلَمُ بِهِمۡۚ قَالَ ٱلَّذِينَ
غَلَبُواْ عَلَىٰٓ أَمۡرِهِمۡ لَنَتَّخِذَنَّ عَلَيۡهِم مَّسۡجِدٗا ﴿٢١﴾

**21.** እንደዚሁም የአላህ ቀጠሮ እርግጠኛ መሆኑን ሰዓቲቱም በእርሷ ጥርጣሬ የሌለ መሆኑን ያውቁ ዘንድ በእነርሱ ላይ ሰዎችን አሳወቅን። አማኞቹና ከሓዲያን ነገራቸውን በመካከላቸው ሲከራከሩ (የሆነውን አስታውስ)። ከሓዲያን በእነርሱ ላይም ግንብን ገንቡ አሉ። ጌታቸው ለእነርሱ ይበልጥ አዋቂ ነው። እነዚያ በነገራቸው ላይ ያሸነፉት ምዕመናን ግን በእነርሱ ላይ በእርግጥ መስጊድን እንሰራለን አሉ።

سَيَقُولُونَ ثَلَٰثَةٞ رَّابِعُهُمۡ كَلۡبُهُمۡ وَيَقُولُونَ خَمۡسَةٞ سَادِسُهُمۡ كَلۡبُهُمۡ رَجۡمَۢا بِٱلۡغَيۡبِۖ وَيَقُولُونَ
سَبۡعَةٞ وَثَامِنُهُمۡ كَلۡبُهُمۡۚ قُل رَّبِّيٓ أَعۡلَمُ بِعِدَّتِهِم مَّا يَعۡلَمُهُمۡ إِلَّا قَلِيلٞۗ فَلَا تُمَارِ فِيهِمۡ إِلَّا مِرَآءٗ
ظَٰهِرٗا وَلَا تَسۡتَفۡتِ فِيهِم مِّنۡهُمۡ أَحَدٗا ﴿٢٢﴾

**22.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሩቅ ወርዋሪዎች ሆነው (ስለ እነርሱ የተወሰኑ ቡድኖች በጥርጣሬ) ሶስት ናቸው አራተኛው ውሻቸው ነው ይላሉ። (ሌሎች ቡድኖች) አምስት ናቸው ስድስተኛው ውሻቸው ነው ይላሉ። (ሶስተኛው ቡድን ደግሞ) ሰባት ናቸው ስምንተኛቸው ውሻቸው ነው ይላሉ። ጌታዬ ቁጥራቸውን ዐዋቂ ነው። ጥቂት ሰው እንጂ አያውቃቸውም በላቸው። እናም በእነርሱ ነገር ግልጽን ክርክር እንጂ ጠልቀህ አትከራከር። በእነርሱም ጉዳይ ከመጽሐፉ ሰዎች አንድንም አትጠይቅ።

وَلَا تَقُولَنَّ لِشَاْيۡءٍ إِنِّي فَاعِلٞ ذَٰلِكَ غَدًا ﴿٢٣﴾ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُۚ وَٱذۡكُر رَّبَّكَ إِذَا نَسِيتَ
وَقُلۡ عَسَىٰٓ أَن يَهۡدِيَنِ رَبِّي لِأَقۡرَبَ مِنۡ هَٰذَا رَشَدٗا ﴿٢٤﴾

**23-24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለማንኛውም ነገር እኔ ይህንን ነገ ሠሪ ነኝ አትበል። አላህ የሻ እንደሆነ እሠራዋለሁ ብትል እንጂ። ይህን ማለት በረሳህ ጊዜ ጌታህን አውሳ። ጌታዬም ከዚህ ይበልጥ ለቀጥታ የቀረበን ሊመራኝ ይከጀላል በላቸው።

ከዋሻው ምዕራፍ ከ (23-24) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ነብዩ በአንድ ነገር ላይ ቃለመሀላ አድርገው ሳይሳካ አርባ ቀን ስለአለፈው በጣም ተከዘው ሳለ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ጦበሪ። በኡመያህ ኢብኑ ኸለፍ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ኢብኑ ከሲር፤ ኢኢብኑ አልጀውዚ፤ ዋሒዲ ና ሱዩጢ)

وَلَبِثُوا۟ فِى كَهْفِهِمْ ثَلَٰثَ مِا۟ئَةٍ سِنِينَ وَٱزْدَادُوا۟ تِسْعًا ﴿٢٥﴾ قُلِ ٱللَّهُ أَعْلَمُ بِمَا لَبِثُوا۟ ۖ لَهُۥ غَيْبُ
ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ أَبْصِرْ بِهِۦ وَأَسْمِعْ ۚ مَا لَهُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَلِىٍّ وَلَا يُشْرِكُ فِى حُكْمِهِۦٓ أَحَدًا ﴿٢٦﴾
وَٱتْلُ مَآ أُوحِىَ إِلَيْكَ مِن كِتَابِ رَبِّكَ ۖ لَا مُبَدِّلَ لِكَلِمَٰتِهِۦ وَلَن تَجِدَ مِن دُونِهِۦ مُلْتَحَدًا ﴿٢٧﴾

**25-27.** በዋሻቸውም ውስጥ ሶስት መቶ ዓመታትን ቆዩ ዘጠኝ አመታትንም ጨመሩ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የቆዩትን ልክ በትክክል አዋቂ ነው በላቸው። የሰማያትና የምድር ሚስጢር የእሱ ብቻ ነው። በእርሱ ምን ያይ፣ ምን ይሰማም! (አላህ ሁሉን ተመልካች ሁሉን ሰሚ መሆኑ ይግረምህ)። ለእነርሱ ከእርሱ በቀር ምንም ወዳጅ የላቸውም። በፍርዱም አንድንም አያጋራም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታህ መጽሀፍ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ። ለቃሎቹ ማንም ለዋጭ የላቸውም። ከርሱም በስተቀር መጠጊያን በፍፁም አታገኝም።

**ከዋሻው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-26) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህን ማመስገን ተገቢ ስለ መሆኑና እኛም ጧት ማታ ማመስገን እንደሚገባን፤
2. በሁሉ ነገር በትክክል መመስገን የሚገባው አላህ እንጂ ማንም እንዳልሆነ፤
3. የቁርአን አስተምህሮት ከሁሉም አስተምህሮቶች የበለጠና ከጉድለቶች ሁሉ የጠራ ስለመሆኑ፤
4. የቁርአን ተልዕኮ አማኞችን ማስተማርና ማክበር ከሓዲያን ማስፈራራትና ማስጠንቀቅ መሆኑን፤
5. በአላህ መዋሸትንና ተገቢ ያልሆኑ ነገሮችን ወደ እርሱ ማስጠጋትን ማውገዝ፤
6. ነብዩ (ﷺ) ሰዎች ቀናውን እንዲከተሉ የነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት ምን ይመስል እንደነበር፤
7. በቁጣና ብስጭት ተነሳስቶ ራስን ማጥፋትና ሰውን መግደል ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
8. በዚህች መሬት ላይ ልዩ ልዩ መዋቢያዎች የመገኘታቸው ፋይዳ ሰዎችን ለመፈተን እንደሆነ፤
9. የአላህ ተዐምራቶች ብዙ መሆናቸውን፤
10. ምድር በላዩ ላይ ያሉ ሁሉ ጠፍተው ባዶ ሁና እንደምትቀር፤
11. ነብዩ (ﷺ) የዋሻ ሰዎችን ታሪክ በማወቃቸውና ለተጠየቁት መልስ በመስጠት ነብይነታቸውን ማረጋገጣቸውን፤
12. የዋሻ ሰዎችን ታሪክ በመጥቀስ ተውሒድን ማስተማር፤
13. አላህ የትክክለኛ አማኝ ባሮቹን ፀሎት እንደሚቀበል፤
14. ሰዎች እምነታቸውን በሰላም ማካሄድ ካልቻሉ መሰደድ ግዴታ እንደሆነ፤
15. ለዲን አስፈላጊውን መስዋዕትነት መክፈል ተገቢ እንደሆነ፤
16. የዋሻ ሰዎችን ታሪክ በመጥቀስ የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማውሳት፤
17. እምነት የሚጨምርና የሚቀንስ መሆኑን፤

18. እውነትን አጥብቆ መያዝ ለሞት ስቃይ የሚዳዳዝ እንኳን ቢሆን ያለው ክብር፤
19. አላህ በዋሻ ሰዎች ታሪክ አማካኝነት ተውሒድን ማስተማሩ፤
20. በግል ጥቅም በዱንያ ጉዳይ ላይ መጓጓት ግፍ እንደሆነ፤
21. ለአላህ ሲሉ መሰደድ ተገቢ ስለመሆኑ፤
22. ሁልጊዜም ወደ አላህ መጠጋት ግዴታ ስለመሆኑ፤
23. አላህ ለወዳጆቹ ያለውን ሰፊ እዝነት በግልፅ መመልከት፤
24. ቀናን መንገድ መያዝና አለመያዝ በአላህ እጅ ብቻ መሆኑን፤
25. የአላህ ፍጡር ሁሉም አስገራሚ ቢሆንም አንዱ ከሌላው የበለጠ አስገራሚ ተግባራት እንዳሉት፤
26. መልካም ጓደኞችን መምረጥ አስፈላጊ ጉዳይ መሆኑን፤
27. የአላህ የሃያልነት የጥበብና የእውቀት መገለጫዎች ማየት፤
28. በምግብና መጠጥ ንፁህ ገንዘብን መፈለግ ተገቢ ስለመሆኑ፤
29. በሺርክ ላይ መሞት ለገሀነም እንደሚጋብዝ፤
30. የመካ ሰወች የካዱትን የሙቶ መነሳት እውነትነት ማረጋገጥ፤
31. በመቃብሮች ላይ መስጊድ መሥራት የሚያስከትለውን አደጋ፤
32. ሰዎች በየጊዜው ያላቸው ባህሪ ተመሳሳይነት የሚሉት መሆናቸውን፤
33. የመፅሐፍት ባለቤቶች ታሪክን በመዘገብ እንደተወናበዱ፤
34. የዋሻ ሰዎች ቁጥር ሰባት እንደሆነና ውሻው ስምንተኛ መሆኑን፤
35. አንድን ነገር ለመሥራት የፈለገ ሰው «አላህ ከፈቀደ» ሳይል «ነገ ይህን አደርጋለሁ» ማለት እንደሌለበትና ከጊዜ በኋላና መርሳቱን ቢያስታውስ እንኳን ይህን ቃል ማለት እንዳለበት፤
36. የዋሻ ሰዎች በዋሻው ውስጥ የቆዩት ሶስት መቶ ዘጠኝ ዓመት መሆኑን የሚሉት ናቸው።

وَٱصۡبِرۡ نَفۡسَكَ مَعَ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ رَبَّهُم بِٱلۡغَدَوٰةِ وَٱلۡعَشِيِّ يُرِيدُونَ وَجۡهَهُۥۖ
وَلَا تَعۡدُ عَيۡنَاكَ عَنۡهُمۡ تُرِيدُ زِينَةَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۖ وَلَا تُطِعۡ مَنۡ أَغۡفَلۡنَا قَلۡبَهُۥ
عَن ذِكۡرِنَا وَٱتَّبَعَ هَوَىٰهُ وَكَانَ أَمۡرُهُۥ فُرُطٗا ٢٨

**28.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ነፍስህንም ከእነዚያ ጌታቸውን ፊቱን ውዴታውን የሚሹ ሆነው በጥዋትና በማታ ከሚገዙት ጋር አስታግስ። የቅርቢቱንም ህይወት ሽልማት የምትሻ ሆነህ አይኖችህ ከእነርሱ ወደ ሌላ አይለፉ። ያ ልቡን እኛን ከማስታወስ ያዘነጋነውንና የግል ፍላጎቱን የተከተለውን ሁሉ ነገር ወሰን ማለፍ የሆነውን ሰው አትታዘዝ።

وَقُلِ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكُمۡۖ فَمَن شَآءَ فَلۡيُؤۡمِن وَمَن شَآءَ فَلۡيَكۡفُرۡۚ إِنَّآ أَعۡتَدۡنَا لِلظَّٰلِمِينَ نَارًا
أَحَاطَ بِهِمۡ سُرَادِقُهَاۚ وَإِن يَسۡتَغِيثُواْ يُغَاثُواْ بِمَآءٖ كَٱلۡمُهۡلِ يَشۡوِي ٱلۡوُجُوهَۚ بِئۡسَ ٱلشَّرَابُ
وَسَآءَتۡ مُرۡتَفَقًا ٢٩

**29.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሰዎች ሆይ)፣ እውነቱ ሁሉ ከጌታችሁ ነው። ስለዚህ የፈለገ ሰው በእውነቱ ይመን። የፈለገ ሰው ይካድ* በላቸው። እኛ ለበደለኛ ከሓዲያን አጥሯ በእነርሱ የከበበ የሆነችውን እሳት አዘጋጅተናል። ከጥም ለመዳን እርዳታን ቢፈልጉ እንደ ዘይት ዝቃጭ ባለ ፊቶችን በሚጠብስ ውሃ ይረዳሉ። መጠጡም ከፋ፣ መደገፊያይቱም ምንኛ አስከፋች!

* ይህ አባባል ለክህደት ፍቃድ መስጠቱ ሳይሆን የዛቻ ቃል ነው እንቢ ካለ ይካድና ዋጋውን ያገኛል ማለት ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ إِنَّا لَا نُضِيعُ أَجۡرَ مَنۡ أَحۡسَنَ عَمَلًا ﴿٣٠﴾
أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهِمُ ٱلۡأَنۡهَٰرُ يُحَلَّوۡنَ فِيهَا مِنۡ أَسَاوِرَ مِن ذَهَبٖ
وَيَلۡبَسُونَ ثِيَابًا خُضۡرٗا مِّن سُندُسٖ وَإِسۡتَبۡرَقٖ مُّتَّكِـِٔينَ فِيهَا عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِۚ
نِعۡمَ ٱلثَّوَابُ وَحَسُنَتۡ مُرۡتَفَقٗا ﴿٣١﴾

**30-31.** እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ እኛ ሥራ ያሳመረን ሰው ምንዳ አናጠፋም። እነዚያ ለእነርሱ የመኖሪያ ገነቶች ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው አሏቸው። በእርሷ ውስጥ ከወርቅ የሆኑ አምባሮች ይሸለማሉ። ከቀጭን ሀርና ከወፍራም ሀር አረንጓዴ ልብሶችን ይለብሳሉ። በውስጧ በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ የተደገፉ ሆነው ይቀመጣሉ። እነዚህ ሰዎች ምንዳቸው ምን ያምር፣ መኖሪያቸው ጀነትም ምንኛ አማረች፣

۞وَٱضۡرِبۡ لَهُم مَّثَلٗا رَّجُلَيۡنِ جَعَلۡنَا لِأَحَدِهِمَا جَنَّتَيۡنِ مِنۡ أَعۡنَٰبٖ وَحَفَفۡنَٰهُمَا بِنَخۡلٖ
وَجَعَلۡنَا بَيۡنَهُمَا زَرۡعٗا ﴿٣٢﴾ كِلۡتَا ٱلۡجَنَّتَيۡنِ ءَاتَتۡ أُكُلَهَا وَلَمۡ تَظۡلِم مِّنۡهُ شَيۡـٔٗاۚ وَفَجَّرۡنَا
خِلَٰلَهُمَا نَهَرٗا ﴿٣٣﴾ وَكَانَ لَهُۥ ثَمَرٞ فَقَالَ لِصَٰحِبِهِۦ وَهُوَ يُحَاوِرُهُۥٓ أَنَا۠ أَكۡثَرُ مِنكَ مَالٗا وَأَعَزُّ
نَفَرٗا ﴿٣٤﴾ وَدَخَلَ جَنَّتَهُۥ وَهُوَ ظَالِمٞ لِّنَفۡسِهِۦ قَالَ مَآ أَظُنُّ أَن تَبِيدَ هَٰذِهِۦٓ أَبَدٗا ﴿٣٥﴾ وَمَآ
أَظُنُّ ٱلسَّاعَةَ قَآئِمَةٗ وَلَئِن رُّدِدتُّ إِلَىٰ رَبِّي لَأَجِدَنَّ خَيۡرٗا مِّنۡهَا مُنقَلَبٗا ﴿٣٦﴾ قَالَ لَهُۥ
صَاحِبُهُۥ وَهُوَ يُحَاوِرُهُۥٓ أَكَفَرۡتَ بِٱلَّذِي خَلَقَكَ مِن تُرَابٖ ثُمَّ مِن نُّطۡفَةٖ ثُمَّ سَوَّىٰكَ
رَجُلٗا ﴿٣٧﴾ لَّٰكِنَّا۠ هُوَ ٱللَّهُ رَبِّي وَلَآ أُشۡرِكُ بِرَبِّيٓ أَحَدٗا ﴿٣٨﴾ وَلَوۡلَآ إِذۡ دَخَلۡتَ جَنَّتَكَ قُلۡتَ

مَا شَآءَ ٱللَّهُ لَا قُوَّةَ إِلَّا بِٱللَّهِۚ إِن تَرَنِ أَنَا۠ أَقَلَّ مِنكَ مَالٗا وَوَلَدٗا ﴿٣٩﴾ فَعَسَىٰ رَبِّيٓ أَن يُؤۡتِيَنِ
خَيۡرٗا مِّن جَنَّتِكَ وَيُرۡسِلَ عَلَيۡهَا حُسۡبَانٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ فَتُصۡبِحَ صَعِيدٗا زَلَقًا ﴿٤٠﴾ أَوۡ يُصۡبِحَ
مَآؤُهَا غَوۡرٗا فَلَن تَسۡتَطِيعَ لَهُۥ طَلَبٗا ﴿٤١﴾ وَأُحِيطَ بِثَمَرِهِۦ فَأَصۡبَحَ يُقَلِّبُ كَفَّيۡهِ عَلَىٰ مَآ
أَنفَقَ فِيهَا وَهِيَ خَاوِيَةٌ عَلَىٰ عُرُوشِهَا وَيَقُولُ يَٰلَيۡتَنِي لَمۡ أُشۡرِكۡ بِرَبِّيٓ أَحَدٗا ﴿٤٢﴾ وَلَمۡ تَكُن
لَّهُۥ فِئَةٞ يَنصُرُونَهُۥ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَمَا كَانَ مُنتَصِرًا ﴿٤٣﴾ هُنَالِكَ ٱلۡوَلَٰيَةُ لِلَّهِ ٱلۡحَقِّۚ هُوَ خَيۡرٞ
ثَوَابٗا وَخَيۡرٌ عُقۡبٗا ﴿٤٤﴾

**32-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለከሓዲያን የሁለትን ሰዎችን ምሳሌ ግለጽላቸው። (ለአንደኛው) ለከሓዲው ሁለት የወይን አትክልቶች አደረግንለት። በዘንባባም አከበብናቸው። በመካከላቸውም አዝመራን አደረግን። ሁለቱም አትክልቶች ሰብላቸውን ሰጡ ከርሱም ምንም አላጎደሉም። በመካከላቸውም ወንዝን አፈሰስን። ለእርሱ ከአትክልቶቹ ሌላ ፍሬያማ ሀብት ነበረው። ለአማኙ ጓደኛው የሚወዳደረው ሲሆን እኔ ከአንተ በገንዘብ ይበልጥ የበዛሁ በወገንም ይበልጥ የበረታሁ ነኝ አለው። እርሱ ነፍሱን በዳይ ሆኖ ወደ አትክልቱ ገባ። ይህች አትክልት መቸም ትጠፋለች ብዬ አልጠረጥርም አለ። ሰዓቲቱንም ትከሰታለች ብዬ አልጠረጥርም እንደምትለው ወደ ጌታዬም ብመለስ ከእርሷ የበለጠን መመለሻ በእርግጥ አገኛለሁ አለው። አማኙ ጓደኛው እርሱ ለእርሱ የሚመላለሰው ሲሆን በዚያ ከአፈር ከዚያ ከፍትወት ጠብታ በፈጠረህ ከዚያ ሰው ባደረገህ ሃያል አምላክ ካድክን? አለው። እኔ ግን አላህ ጌታዬ ነው እላለሁ። በጌታዬም አንድንም አላጋራም። ወደ አትክልትህ በገባህ ጊዜ አላህ የሻው ይሆናል። በአላህ ቢሆን እንጂ ብልሃትም የለም አትልም ኖሯልን? እኔን በገንዘብም ሆነ በልጅ ከአንተ በጣም ያነስኩ ሆኜ ብታየኝ ጌታዬ ከአትክልትህ የበለጠን ሊሰጠኝ በአትክልትህ ላይ በሰማይ መብረቆችን ሊልክባትና የምታንዳልጥ ምልጥ ምድር ልትሆን ይቻላል። ወይም ውሃው ሰራጊ ሊሆን ይችላል። ያን ጊዜ እርሱን መፈለግ ፈጽሞ አትችልም አለው። ሀብቱም ጠፋ። እርሷ በዳሶችዋ ላይ የወደቀች ሆና በእርሷ ባወጣው ገንዘብ ላይ የተፀፀተ መዳፎቹን የሚያገላብጥና ወይ ፀፀቴ፣ በጌታዬ አንድንም ባላጋራሁ የሚል ነው። እርሱ ከአላህ ሌላ የሚረዱት ጭፍሮች አልነበሩትም። ተረጂም አልነበረም። እዚያ ዘንድ በትንሳኤ ቀን ስልጣኑ እውነተኛ ለሆነው ለአላህ ብቻ ነው። እርሱ በመመንዳት የበለጠ ፍጻሜንም በማሳመር የበለጠ ነው።

وَٱضۡرِبۡ لَهُم مَّثَلَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا كَمَآءٍ أَنزَلۡنَٰهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَٱخۡتَلَطَ بِهِۦ نَبَاتُ ٱلۡأَرۡضِ
فَأَصۡبَحَ هَشِيمٗا تَذۡرُوهُ ٱلرِّيَٰحُۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ مُّقۡتَدِرًا ٤٥

45. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነርሱም የቅርቢቱን ህይወት ምሳሌ አውሳላቸው። እርሷ ከሰማይ እንዳወረድነው ውሃ በእርሱም የምድር ቡቃያ እንደተቀላቀለበት ከተዋበ በኋላ ደርቆ ንፋሶችም የሚያበኑት ደቃቅ እንደሆነ ብጤ ናት። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

ٱلۡمَالُ وَٱلۡبَنُونَ زِينَةُ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَاۖ وَٱلۡبَٰقِيَٰتُ ٱلصَّٰلِحَٰتُ
خَيۡرٌ عِندَ رَبِّكَ ثَوَابٗا وَخَيۡرٌ أَمَلٗا ٤٦

46. ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ህይወት ጌጦች ብቻ ናቸው። መልካም ቀሪ ሥራዎች ግን በጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው። በተስፋም በላጭ ናቸው።

وَيَوۡمَ نُسَيِّرُ ٱلۡجِبَالَ وَتَرَى ٱلۡأَرۡضَ بَارِزَةٗ وَحَشَرۡنَٰهُمۡ فَلَمۡ نُغَادِرۡ مِنۡهُمۡ أَحَدٗا ٤٧
وَعُرِضُواْ عَلَىٰ رَبِّكَ صَفّٗا لَّقَدۡ جِئۡتُمُونَا كَمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ أَوَّلَ مَرَّةِۭۚ بَلۡ زَعَمۡتُمۡ أَلَّن نَّجۡعَلَ
لَكُم مَّوۡعِدٗا ٤٨ وَوُضِعَ ٱلۡكِتَٰبُ فَتَرَى ٱلۡمُجۡرِمِينَ مُشۡفِقِينَ مِمَّا فِيهِ
وَيَقُولُونَ يَٰوَيۡلَتَنَا مَالِ هَٰذَا ٱلۡكِتَٰبِ لَا يُغَادِرُ صَغِيرَةٗ وَلَا كَبِيرَةً إِلَّآ أَحۡصَىٰهَاۚ
وَوَجَدُواْ مَا عَمِلُواْ حَاضِرٗاۗ وَلَا يَظۡلِمُ رَبُّكَ أَحَدٗا ٤٩

47-49. ተራራዎችን የምናስኬድበትን ቀን (አስታውስ)። ምድርንም ግልጽ ሆና ታያታለህ። እንሰበስባቸዋለንም። ከእነርሱ አንድንም አንተውም። የተሰለፉ ሆነው በጌታህ ላይ ይቀርባሉ። (ይባላሉም) በመጀመሪያ ጊዜ እንደፈጠርናችሁ ራቁታችሁን በእርግጥ ወደ እኛ መጣችሁ። በእውነቱ ለእናንተ የመቀስቀሻ ጊዜን አናደርግም መስሏችሁ ነበር። ለሰው ሁሉ መጽሐፉ ይቀርባል። ወዲያውም ከሓዲያንን በውስጡ ካለው ነገር ፈሪዎች ሆነው ታያቸዋለህ። ዋ፣ ጥፋታችን ይህ መጽሐፍ ከሥራ ትንሽንም ትልቅንም የቆጠራት ቢሆን እንጂ የማይተወው ምን አለው? ይላሉ። የሠሩትንም ነገር ሁሉ ቅርብ ሆኖ ያገኙታል። ጌታህም አንድንም አይበድልም።

وَإِذۡ قُلۡنَا لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ كَانَ مِنَ ٱلۡجِنِّ فَفَسَقَ عَنۡ أَمۡرِ رَبِّهِۦٓۗ
أَفَتَتَّخِذُونَهُۥ وَذُرِّيَّتَهُۥٓ أَوۡلِيَآءَ مِن دُونِي وَهُمۡ لَكُمۡ عَدُوُّۢۚ بِئۡسَ لِلظَّٰلِمِينَ بَدَلٗا ﴿٥٠﴾ ۞ مَّآ
أَشۡهَدتُّهُمۡ خَلۡقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَلَا خَلۡقَ أَنفُسِهِمۡ وَمَا كُنتُ مُتَّخِذَ ٱلۡمُضِلِّينَ عَضُدٗا ﴿٥١﴾

**50-51.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለመላዕክት ለአደም ስገዱ ባልናቸው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡፡ ወዲያውም ኢብሊስ ብቻ ሲቀር ሰገዱ፡፡ ከአጋንንት ነሳ ነበር ከጌታውም ትዕዛዝ ወጣ እርሱንና ዘሮቹን እነርሱም ለእናንተ ጠላቶች ሲሆኑ ከኔ ሌላ ረዳቶች አድርጋችሁ ትይዛላችሁን? ለበዳዮች ልዋጭነቱ ከፋ፡፡ የሰማያትና የምድርም አፈጣጠር አላሰየኋቸውም፡፡ የነፍሶቻቸውንም አፈጣጠር እንደዚሁ አሳሳቾችንም ረዳቶች አድርጌ የምይዝ አይደለሁም፡፡

وَيَوۡمَ يَقُولُ نَادُواْ شُرَكَآءِيَ ٱلَّذِينَ زَعَمۡتُمۡ فَدَعَوۡهُمۡ فَلَمۡ يَسۡتَجِيبُواْ لَهُمۡ وَجَعَلۡنَا بَيۡنَهُم
مَّوۡبِقٗا ﴿٥٢﴾ وَرَءَا ٱلۡمُجۡرِمُونَ ٱلنَّارَ فَظَنُّوٓاْ أَنَّهُم مُّوَاقِعُوهَا وَلَمۡ يَجِدُواْ عَنۡهَا مَصۡرِفٗا ﴿٥٣﴾

**52-53.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያንም አምላክ የምትሏቸውን ተጋሪዎቼን ጥሩ የሚልበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ይጠሯቸዋልም ግን አይመልሱላቸውም፡፡ በመካከላቸውም መጥፊያን ስፍራ ገሀነምንም አደረግን፡፡ ከሓዲያንም እሳትን ያያሉ እነርሱም በውስጧ ወዳቂዎች መሆናቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ ከእርሷም መሸሻን አያገኙም፡፡

وَلَقَدۡ صَرَّفۡنَا فِي هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانِ لِلنَّاسِ مِن كُلِّ مَثَلٖۚ وَكَانَ ٱلۡإِنسَٰنُ أَكۡثَرَ شَيۡءٖ جَدَلٗا ﴿٥٤﴾
وَمَا مَنَعَ ٱلنَّاسَ أَن يُؤۡمِنُوٓاْ إِذۡ جَآءَهُمُ ٱلۡهُدَىٰ وَيَسۡتَغۡفِرُواْ رَبَّهُمۡ إِلَّآ أَن تَأۡتِيَهُمۡ سُنَّةُ
ٱلۡأَوَّلِينَ أَوۡ يَأۡتِيَهُمُ ٱلۡعَذَابُ قُبُلٗا ﴿٥٥﴾

**54-55.** በዚህም ቁርኣን ውስጥ ከየምሳሌው ሁሉ ለሰዎች መላልሰን ገለጽን ሰውም ከነገሩ ሁሉ ይበልጥ ክርክረ ብዙ ነው፡፡ ሰዎችንም መመሪያ በመጣላችሁ ጊዜ ከማመንና ጌታቸውንም ምህረትን ከመለመን የከለከላቸው የመጀመሪያዎቹ ህዝቦች ልማድ መጥፋት ልትመጣባቸው ወይም ቅጣቱ በየዓይነቱ ሊመጣባቸው መጠባበቅ እንጂ ሌላ አልከለከላቸውም፡፡

وَمَا نُرۡسِلُ ٱلۡمُرۡسَلِينَ إِلَّا مُبَشِّرِينَ وَمُنذِرِينَۚ وَيُجَٰدِلُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِٱلۡبَٰطِلِ لِيُدۡحِضُواْ
بِهِ ٱلۡحَقَّۖ وَٱتَّخَذُوٓاْ ءَايَٰتِي وَمَآ أُنذِرُواْ هُزُوٗا ٥٦ وَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّن ذُكِّرَ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِۦ فَأَعۡرَضَ
عَنۡهَا وَنَسِيَ مَا قَدَّمَتۡ يَدَاهُۚ إِنَّا جَعَلۡنَا عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ أَكِنَّةً أَن يَفۡقَهُوهُ وَفِيٓ ءَاذَانِهِمۡ وَقۡرٗاۖ
وَإِن تَدۡعُهُمۡ إِلَى ٱلۡهُدَىٰ فَلَن يَهۡتَدُوٓاْ إِذًا أَبَدٗا ٥٧

**56-57.** መልዕክተኞችንም አብሳሪዎችና አስፈራሪዎች ሆነው እንጂ አንልክም። እነዚያ የካዱትም በውሸት እውነቱን በእሱ ሊያበላሹ ይከራከራሉ አንቀፆቼንና በእርሱ የተስፈራሩበትንም ነገር ማላገጫ አድርገው ያዙ። በጌታውም አንቀፆች ከተገሰፀና ከእርሷ ከዞረ ሁለት እጆቹም ያስቀደሙትን ነገር ከረሳቸውም ይበልጥ በዳይ ማን ነው? እኛ በልቦቻቸው ላይ እንዳያውቁት ሽፋኖችን በጆሮዎቻቸውም ውስጥ ድንቁርናን አደረግን ወደ መመራትም ብትጠራቸው ያን ጊዜ ፈጽሞ አይመሩም።

وَرَبُّكَ ٱلۡغَفُورُ ذُو ٱلرَّحۡمَةِۖ لَوۡ يُؤَاخِذُهُم بِمَا كَسَبُواْ لَعَجَّلَ لَهُمُ ٱلۡعَذَابَۚ
بَل لَّهُم مَّوۡعِدٞ لَّن يَجِدُواْ مِن دُونِهِۦ مَوۡئِلٗا ٥٨ وَتِلۡكَ ٱلۡقُرَىٰٓ أَهۡلَكۡنَٰهُمۡ لَمَّا ظَلَمُواْ
وَجَعَلۡنَا لِمَهۡلِكِهِم مَّوۡعِدٗا ٥٩

**58-59.** ጌታህም በጣም መሀሪው የእዝነት ባለቤቱ ነው። በሠሩት ሥራ ቢይዛቸው ኖሮ ቅጣቱን ለእነርሱ ባስቸኮለባቸው ነበር። ግን ለእነርሱ ከእርሱ ሌላ መጠጊያን ፈጽሞ የማያገኙበት ቀጠሮ አላቸው። እነዚህ ከተሞችም በበደሉ ጊዜ አጠፋናቸው ለመጥፊያቸውም የተወሰነ ጊዜ አደረግን።

وَإِذۡ قَالَ مُوسَىٰ لِفَتَىٰهُ لَآ أَبۡرَحُ حَتَّىٰٓ أَبۡلُغَ مَجۡمَعَ ٱلۡبَحۡرَيۡنِ أَوۡ أَمۡضِيَ حُقُبٗا ٦٠ فَلَمَّا بَلَغَا
مَجۡمَعَ بَيۡنِهِمَا نَسِيَا حُوتَهُمَا فَٱتَّخَذَ سَبِيلَهُۥ فِي ٱلۡبَحۡرِ سَرَبٗا ٦١ فَلَمَّا جَاوَزَا قَالَ لِفَتَىٰهُ
ءَاتِنَا غَدَآءَنَا لَقَدۡ لَقِينَا مِن سَفَرِنَا هَٰذَا نَصَبٗا ٦٢ قَالَ أَرَءَيۡتَ إِذۡ أَوَيۡنَآ إِلَى ٱلصَّخۡرَةِ فَإِنِّي
نَسِيتُ ٱلۡحُوتَ وَمَآ أَنسَىٰنِيهُ إِلَّا ٱلشَّيۡطَٰنُ أَنۡ أَذۡكُرَهُۥۚ وَٱتَّخَذَ سَبِيلَهُۥ فِي ٱلۡبَحۡرِ عَجَبٗا ٦٣
قَالَ ذَٰلِكَ مَا كُنَّا نَبۡغِۚ فَٱرۡتَدَّا عَلَىٰٓ ءَاثَارِهِمَا قَصَصٗا ٦٤ فَوَجَدَا عَبۡدٗا مِّنۡ عِبَادِنَآ ءَاتَيۡنَٰهُ
رَحۡمَةٗ مِّنۡ عِندِنَا وَعَلَّمۡنَٰهُ مِن لَّدُنَّا عِلۡمٗا ٦٥

**60-65.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳ*[1] ለወጣቱ*[2] የሁለቱን ባህሮች መገናኛ እስከምደርስ ወይም ብዙን ጊዜ እስከምሄድ ድረስ ከመጓዝ አልወገድም ያለውን (አስታውስ)። የሁለቱን ባህር መገናኛ*[3] በደረሱም ጊዜ ዓሳቸውን ረሱ ዓሳው መንገዱንም በባህር ውስጥ ቀዳዳ አድርጎ ያዘ። ባለፉም ጊዜ ለወጣቱ ምሳችንን ስጠን ከዚህ ጉዟችን በእርግጥ ድካምን አግኝተናልና አለ። አየህን? ወደ ቋጥኟ በተጠጋን ጊዜ እኔ ዐሳውን ረሳሁ ማስታወሱንም ሰይጣን እንጂ ሌላ አላስረሳኝም በባህሩም ውስጥ መንገዱን አስደናቂ መንገድ አድርጎ ያዘ አለ። ሙሳ ይህ እኮ እንፈልገው የነበረው ነው አለው።*[4] ከዚያ በኮቴዎቻቸው (ዱካቸው) ላይ እየተከተሉ ተመለሱ። ከባሮቻችን ከእኛ ዘንድ ችሮታን*[5] የሰጠነውን ከኛም ዘንድ እውቀትን ያስተማርነውን አንድን ባሪያችንን አገኙ።

*1 ነብዩ ሙሳ ኢብኑ ዒምራን ወደ ፈርዖን ተልከው የነበሩት ናቸው።

*2 ዩሸዕ ኢብኑ ኑን ይባል ነበር ነብዩ ሙሳ ኢብኑ ዒምራን ጋር አይለይም ነበር።

*3 ይህ ቦታ የት እንደሆነ የተፍሲር ምሁራን ብዙ ብለዋል። የሮምና የፋርስ ባህር፤ የኡርዱን ባህር ጦንጃ አጠገብ ያለው ባህር፤ የአፍሪካ ባህር የሚል ነው። ነጭ ባህርና ቀይ ባህር የሚልም አለ ነገር ግን ቦታውን ለይቶ ማወቁ ጠቀሜታ ቢኖረው ኖሮ አላህ እራሱ በገለፀው ነበር። ሆኖም ስሙ ኸዲር ለመባሉ አያሌ መረጃዎች አሉ።

*4 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ የሙሳን ታሪክ አስመልክቶ ሰዒድ ኢብኑ ጁበይር እንዳስተላለፉት «ለኢብኑ ዐብባስ «ነውፍ አል. በካሊ የተባለው ሰው ሙሳ የኸድርን ባልንጀራ ናቸው እንጂ ከእስራኤላዊያን ልጆች መካከል አይደሉም እያለ ያወራል» አልኳቸው። ኢብኑ ዐብባስም «የአላህ ጠላት ዋሽቷል ኡበይ ብኑ ከዕብ እንደነገረኝ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰምቷል፦ «ሙሳ በእስራኤላዊያን ልጆች ፊት ንግግር ሊያደርግ ተነሳ «የትኛው ሰው ነው አዋቂ?» ተብሎም ተጠየቀ። እሱም «እኔ ነኝ» አላቸው። አላህም እውቀትን ሁሉ ወደርሱ ወደ አላህ ስላስጠጋ ሙሳን ገሰፃቸው። አላህም መለኮታዊ ራዕይ ወደ ሙሳ እንዲህ ሲል ላከ «በሁለት ባህሮች መተላለፊያ ላይ ካንተ በላይ አዋቂ የሆነ ባሪያችን አለ።» ሙሳም «ጌታዬ ሆይ! እንዴት ልገናኘው እችላለሁ?» ሲል ጠየቀ። እንዲህም ተባለ «ዓሳ ውሰድና ቅርጫት ውስጥ አድርገህ መንገድህን ቀጥል። ዓሳውን ስታጣ እሱን ታገኘዋለህ።» ሙሳም ዓሳን ቅርጫት ውስጥ ካደረገ በኋላ ዩሸዕ ብኑ ኑን ከተባለው ወጣት ጋር አብረው ጉዟቸውን ቀጠሉ። አንድ ቋጥኝም አጠገብ ደርሰው ደገፍ ብለው ተኙ። ዓሳ ቅርጫት ውስጥ እያለ ተንቀሳቀሰና ከቅርጫት ውስጥ በመውጣት ባህር ውስጥ ገባ በዚያውም በባህሩ ውስጥ ቀዳዳ አድርጎ ያዘ። አላህም የወንዙን መፍሰስ በዓሳ ሰበብ አቆመው እንደ ቦይም አድርጎ ቀጥ ባለው ውሃ ዓሳው ጉዞውን ቀጠለ። ከእንቅልፋቸው ሲነቁ ባልንጀራቸው ስለ ዓሳው የሚነግራቸውን ነገር ረሳውና የተቀሩትን ለሊቶችና ቀናት ተጓዙ። በሚቀጥለው ቀን ጠዋት ሙሳ ይህን ወጣት «ምሳችንን ስጠን ከዚህም ጉዟችን በእርግጥ ድካምን አግኝተናልና» አሉ። ወጣቱም «አየህን? ወደ ቋጥኝዋ በተጠጋን ጊዜ እኔ ዓሳውን ረሳሁ፤ ማስታወሱንም ሰይጣን እንጂ ሌላ አላስረሳኝም። በባህሩ ውስጥም መንገዱን አስደናቂ መንገድ አድርጎ ያዘ» አለ። ለዓሳው መንገድ ነበር። ለሙሳና ለወጣቱም አስደናቂ ነገር ነበር። «ሙሳም ይህ እንፈልግ የነበረው ነው አለው፤ በፈለጎቻቸውም ላይ እየተከተሉ ተመለሱ።» አል. ከህፍ 64 ሁለቱም ወደ ኋላ ተመለሱ፤ ወደ ቋጥኙ እስኪደርሱ ድረስም ተጓዙ። እነሆም አንድ በጨርቅ የተሸፈነ ሰውም አገኙ። ሙሳም

ለሰውየው ሰላምታ ሰጡት። ኺድርም ለሙሳ በጣም በመገረም ሁኔታ «በምድራችን ላይ ሰላም አለን?» ብሎ ጠየቋቸው። ሙሳም «እኔ ሙሳ ነኝ» አሏቸው። «ሙሳ የኢስራኤላውያን ልጆች?» ሲሉ አሁንም ኺድር ሙሳን በመገረም ጠየቁ። ሙሳም «አዎን ነኝ ከተማርከው ቀጥተኛን ዕውቀት ታስተምረኝ ዘንድ ወደ አንተ መጥቻለሁ» አሉት። ኺድርም «አንተ ከእኔ ጋር መታገስን በጭራሽ አትችልም። ሙሳ ሆይ! እኔ አንተ የማታውቀው ነገር ግን አላህ ያሳወቀኝ የሆነ እውቀት አለኝ። አንተ ደግሞ አላህ ያሳወቀህን ነገር ንገረኝ እኔ የማላውቀው ዕውቀት አለህ» አሏቸው። ሙሳም «አላህ የሻ እንደሆነ ታጋሽና ላንተ ታዛዥ ሆኜ ታገኘኛለህ» አሉት። ኺድርም «ብትከተለኝም ለአንተ ከርሱ ማውሳትን እስከምጀምርልህ ድረስ ምንም ነገር አትጠይቀኝ» አሉት። በባህርዳርቻውም ላይ መጓዝ ጀመሩ። መርከብ በአጠገባቸውም አለፈች። እንዲያሳፍሯቸው ሲጠየቁ ሰዎች ኺድር መሆናቸው ስላወቁ ካለምንም ክፍያ አሳፈሯቸው። በመርከቧ እየተጓዙ ሳሉም ኺድር የመርከቧን አንድ ክፍል በመጥረቢያ ሲፈልጡ ሙሳ ተመልክተው «ባለቤቶቿን ልታሰምጥ ቀደድካትን? ትልቅ ነገርን በእርግጥ ሰራህ» አሉት። ኺድርም «አንተ ከኔ ጋር ትዕግስትን ፈፅሞ አትችልም አላልኩምን? አሉ። ሙሳም «በረሳሁት ነገር አትያዘኝ ችግርን አታሸክመኝ» አሉት። የአላህ መልዕክተኛ «ይህ የሙሳ የመጀመሪያው መርሳት ነው» አሉ። ሙሳና ኺድር በመርከቧ እየተጓዙ ሳለ አንዲት ወፍ በመርከቧ ጠረፍ ላይ አረፈችና በምንቃሯ ከባህሩ ጠጣች። ይህን በተመለከቱ ጊዜ ኺድር እንዲህ አሉ «የኔ ዕውቀትና ያንተ ዕውቀት ከአላህ ዕውቀት ጋር ሲነፃፀር ይህች ወፍ ከባህሩ ውሃ ብትጠጣ እንደማይቀንሰው አይነት ነው» አሏቸው። ወደ ባህር ዳርቻ ደርሰው ሁለቱም ከመርከቧ ወርደው በየብስ ላይ ጉዟቸውን ቀጠሉ። ሁለቱም ኺድርና ሙሳ እየተጓዙ ሳለ ኺድር ከሕፃናት ጋር አብሮ የሚጫወት አንድ ሕፃን ተመለከቱና ጭንቅላቱን ይዘው በእጃቸው ስበው ከሰውነቱ በማለያየት ገደሉት። ሙሳም ይህን ተመልክተው «ያለ ነፍስ መግደል ንፁህን ነፍስ ገደልክን?» በእርግጥ መጥፎ ነገርን ሰራህ» አሏቸው። ኺድርም «አንተ ከእኔ ጋር ትዕግስትን ፈፅሞ አትችልም አላልኩህምን?» አሏቸው። የሐዲስ አስተላላፊው እንዳሉት «ይህ ከበፊቱ የበለጠና ከበድ ያለ ተግሳፅ ነው» ሙሳም «ከርሷ ከአሁኒቱ ሰዓት በኋላም ከምንም ነገር ብጠይቅህ ከኔ የይቅርታን መጨረሻ በእርግጥ ይደርስሃል» አሉት። ሄዱም ወደ አንዲት ከተማ በመጡም ጊዜ ነዋሪዎቿን ምግብን ጠየቁ ከማስተናገዳቸውም እምቢ አሉ። በርሷም ውስጥ ለመውደቅ የተቃረበን ግድግዳ አገኙ። ኺድርም በእጃቸው አቆሙት። ሙሳም «እነዚህ ሰዎች ወደነርሱ መጥተን ሳለ ምግብ አላበሉንም በእንግድነትም አላስተናገዱንም በሻህ ኖሮ በነርሱ ላይ ዋጋን በተቀበልክ ነበር» አሏቸው። ኺድርም «ይህ በኔና ባንተ መካከል መለያያ ነው። በርሱ ላይ መታገስን ያልታገስክበትን ፍቺ እነግርሃለሁ። መርከቢቱም በባህሩ ለሚሰሩ ምስኪኖች ነበረች፤ ከኋላቸውም መርከብን ሁሉ በቅሚያ የሚይዝ ንጉስ ነበርና እንዳይቀማቸው ላነውራት ፈቀድኩ። ወጣቱ ልጅማ ወላጆቹ ምዕመናን ነበሩ። ቢያድግ ትዕቢትንና ክህደትንም የሚያስገድዳቸው መሆኑን ፈራን፤ ጌታቸውንም በንፁህነት ከርሱ በላጭን ከእዝነትም ከርሱ በጣም ቀራቢ ልጅ ሊለው ጥላቸውን ፈለግን። ግድግዳውማ በከተማይቱ ውስጥ የነበሩ የሁለቱ የቲሞች ድሃ አደጎች ወጣቶች ነበር። በስሩም ለነርሱ የሆነ የተቀበረ ድልብ ነበር። አባታቸውም መልካም ሰው ነበር ጌታህ ለአካለ መጠን እንዲደርሱና ከጌታህ ችሮታ ድልባቸውን እንዲያወጡ ፈቀደ። በፈቃዱም አለው ሰራሁትም ይህ በርሱ ላይ መታገስን ያልቻልከው ነገር ፍቺ ነው» አሉት። የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ አሉ፤ «አላህ የሁለቱን ታሪክ እስኪፈፅምልን ድረስ ሙሳ ታግሰው በነበረ ወደድን።»

✷5 ችሮታን የሚለው ቃል ነብይነትን ወይም ከፍተኛ ማዕረግን ማለት ነው በሚል የተወሰኑ ክርክሮች አሉ። ከዚህም በመነሳት እኚህ ሰው ነብይ ነበሩ ወይስ አልነበሩም በሚል የምሁራን ልዩነቶች አሉ። ይህ ሰው ስሙ ኺድር መሆናቸውን ሁሉም የተፍሲር ምሁራን ተስማምተዋል።

قَالَ لَهُۥ مُوسَىٰ هَلۡ أَتَّبِعُكَ عَلَىٰٓ أَن تُعَلِّمَنِ مِمَّا عُلِّمۡتَ رُشۡدٗا ﴿٦٦﴾ قَالَ إِنَّكَ لَن تَسۡتَطِيعَ
مَعِيَ صَبۡرٗا ﴿٦٧﴾ وَكَيۡفَ تَصۡبِرُ عَلَىٰ مَا لَمۡ تُحِطۡ بِهِۦ خُبۡرٗا ﴿٦٨﴾ قَالَ سَتَجِدُنِيٓ إِن شَآءَ ٱللَّهُ
صَابِرٗا وَلَآ أَعۡصِي لَكَ أَمۡرٗا ﴿٦٩﴾ قَالَ فَإِنِ ٱتَّبَعۡتَنِي فَلَا تَسۡـَٔلۡنِي عَن شَيۡءٍ حَتَّىٰٓ أُحۡدِثَ لَكَ
مِنۡهُ ذِكۡرٗا ﴿٧٠﴾

**66-70.** ሙሳ ለእርሱ ከተማርከው ነገር ቀጥተኛን እውቀት ታስተምረኝ ዘንድ ልከተልህ? አለው፡፡ (ባሪያውም) አንተ ከእኔ ጋር መታገስን በጭራሽ አትችልም አለው፡፡ በእውቀትም በእርሱ ባላደረስከው ነገር ላይ እንዴት ትታገሳለህ፡፡ ሙሳ አላህ የፈለገ እንደሆነ ታጋሽና ለአንተ ትዕዛዝን የማልጥስ ሆኜ ታገኘኛለህ አለው፡፡ ብትከተለኝም ለአንተ ከእርሱ ማውሳትን እስከምጀምርልህ ድረስ ከምንም ነገር አትጠይቀኝ አለው፡፡

فَٱنطَلَقَا حَتَّىٰٓ إِذَا رَكِبَا فِي ٱلسَّفِينَةِ خَرَقَهَاۖ قَالَ أَخَرَقۡتَهَا لِتُغۡرِقَ أَهۡلَهَا لَقَدۡ جِئۡتَ شَيۡـًٔا
إِمۡرٗا ﴿٧١﴾ قَالَ أَلَمۡ أَقُلۡ إِنَّكَ لَن تَسۡتَطِيعَ مَعِيَ صَبۡرٗا ﴿٧٢﴾ قَالَ لَا تُؤَاخِذۡنِي بِمَا نَسِيتُ
وَلَا تُرۡهِقۡنِي مِنۡ أَمۡرِي عُسۡرٗا ﴿٧٣﴾

**71-73.** ሄዱም፡፡ በመርከቢቱም በተሳፈሩ ጊዜ መርከቢቱን ቀደዳት፡፡ ባለቤቶችዋን ልታሰጥም ቀደድካትን? ትልቅን ጥፋት በእርግጥ ሠራህ አለው፡፡ አንተ ከእኔ ጋር ትዕግስትን ፈጽሞ አትችልም አላልኩምን? አለ፡፡ በረሳሁት* ነገር አትያዝብኝ፡፡ ከነገሬም ችግርን አታሸክመኝ አለው፡፡

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሰው ፆመኛ ሆኖ ሳለ ረስቶ ቢበላ ፆሙን ይጨርስ፤ አላህ ነው ያበላው ያጠጣውም» ብለዋል፡፡

فَٱنطَلَقَا حَتَّىٰٓ إِذَا لَقِيَا غُلَٰمٗا فَقَتَلَهُۥ قَالَ أَقَتَلۡتَ نَفۡسٗا زَكِيَّةَۢ بِغَيۡرِ نَفۡسٖ
لَّقَدۡ جِئۡتَ شَيۡـٔٗا نُّكۡرٗا ﴿٧٤﴾

**74.** ወርደው ተጓዙም ወጣቱንም ልጅ ባገኘውና በገደለው ጊዜ ነፍስን ያልገደለችን ንፁህን ነፍስ ገደልክን? በእርግጥ መጥፎን ነገር ሰራህ አለው፡፡

۞ قَالَ أَلَمۡ أَقُل لَّكَ إِنَّكَ لَن تَسۡتَطِيعَ مَعِيَ صَبۡرٗا ﴿٧٥﴾ قَالَ إِن سَأَلۡتُكَ عَن شَيۡءِۭ بَعۡدَهَا
فَلَا تُصَٰحِبۡنِيۖ قَدۡ بَلَغۡتَ مِن لَّدُنِّي عُذۡرٗا ﴿٧٦﴾

**75-76.** አንተ ከእኔ ጋር ትዕግስትን ፈጽሞ አትችልም አላልኩህምን? አለ። ከአሁኒቱ ጊዜ በኋላ ከምንም ነገር ብጠይቅህ አትጎዳኘኝ። ከእኔ የይቅርታን መጨረሻ በእርግጥ ደርሳሀል አለው።

فَٱنطَلَقَا حَتَّىٰٓ إِذَآ أَتَيَآ أَهۡلَ قَرۡيَةٍ ٱسۡتَطۡعَمَآ أَهۡلَهَا فَأَبَوۡاْ أَن يُضَيِّفُوهُمَا فَوَجَدَا فِيهَا جِدَارٗا
يُرِيدُ أَن يَنقَضَّ فَأَقَامَهُۥۖ قَالَ لَوۡ شِئۡتَ لَتَّخَذۡتَ عَلَيۡهِ أَجۡرٗا ﴿٧٧﴾ قَالَ هَٰذَا فِرَاقُ بَيۡنِي وَبَيۡنِكَۚ
سَأُنَبِّئُكَ بِتَأۡوِيلِ مَا لَمۡ تَسۡتَطِع عَّلَيۡهِ صَبۡرًا ﴿٧٨﴾ أَمَّا ٱلسَّفِينَةُ فَكَانَتۡ لِمَسَٰكِينَ يَعۡمَلُونَ فِي
ٱلۡبَحۡرِ فَأَرَدتُّ أَنۡ أَعِيبَهَا وَكَانَ وَرَآءَهُم مَّلِكٞ يَأۡخُذُ كُلَّ سَفِينَةٍ غَصۡبٗا ﴿٧٩﴾ وَأَمَّا ٱلۡغُلَٰمُ فَكَانَ
أَبَوَاهُ مُؤۡمِنَيۡنِ فَخَشِينَآ أَن يُرۡهِقَهُمَا طُغۡيَٰنٗا وَكُفۡرٗا ﴿٨٠﴾ فَأَرَدۡنَآ أَن يُبۡدِلَهُمَا رَبُّهُمَا خَيۡرٗا مِّنۡهُ
زَكَوٰةٗ وَأَقۡرَبَ رُحۡمٗا ﴿٨١﴾ وَأَمَّا ٱلۡجِدَارُ فَكَانَ لِغُلَٰمَيۡنِ يَتِيمَيۡنِ فِي ٱلۡمَدِينَةِ وَكَانَ تَحۡتَهُۥ كَنزٞ لَّهُمَا
وَكَانَ أَبُوهُمَا صَٰلِحٗا فَأَرَادَ رَبُّكَ أَن يَبۡلُغَآ أَشُدَّهُمَا وَيَسۡتَخۡرِجَا كَنزَهُمَا رَحۡمَةٗ مِّن رَّبِّكَۚ وَمَا
فَعَلۡتُهُۥ عَنۡ أَمۡرِيۚ ذَٰلِكَ تَأۡوِيلُ مَا لَمۡ تَسۡطِع عَّلَيۡهِ صَبۡرٗا ﴿٨٢﴾

**77-82.** ሄዱም ወደ አንዲት ከተማ ሰዎች ዘንድ ደረሱ ከነዋሪዎች ምግብን ጠየቁ። ከማስተናገዳቸውም እምቢ አሉ። በእርሷም ውስጥ ለመውደቅ የተቃረበን ግድግዳ አገኙ። (ኸድር) አቆመው። ሙሳ ብትፈልግ ኖሮ በእርሱ ላይ ዋጋን በተቀበልክ ነበር አለው። (ኸድር) ይህ በኔና በአንተ መካከል መለያያችን ነው በእርሱ ላይ መታገስን ያልቻለክበትን ፍቺ እነግርሃለሁ። መርከቢቱማ በባህር ውስጥ ለሚሠሩ ምስኪኖች ነበረች። ከኋላቸው መርከብን ሁሉ በቅሚያ የሚወስድ ክፉ ንጉስ ነበረና እንዳይቀማቸው ላስነውራት ፈልጌ ነው። ያ፣ ወጣቱ ልጅማ ወላጆቹ ምዕመናን ነበሩ። ቢያድግ በትዕቢትና በክህደት ወላጆቹን የሚያስገድዳቸው መሆኑን ፈራን። ጌታቸው በንፁሕነት ከእርሱ በላጭን በእዝነትም ከእርሱ በጣም ቀራቢን ልጅ ሊለውጥላቸው ፈለግን። ግድግዳው በከተማይቱ ውስጥ የነበሩ የሁለት የቲሞች ወጣቶች ነበር። በስሩም ለእነርሱ የሆነ የተቀበረ ድልብ ነበረና አባታቸውም መልካም ሰው ነበር። ጌታህም ለአካለ መጠን እንዲደርሱና ከጌታህ ችሮታ ድልባቸውን እንዲያወጡ ፈቀደ። በፈቃዴም አልሠራሁትም። ይህ ያ በእርሱ ላይ መታገስን ያልቻልከው ነገር ፍች ነው አለው።*

* ነብዩ (ﷺ)፦ «በእኛና በሙሳ ላይ የአላህ ረህመት ይሁን። ታግሶ ቢሆን ኑሮ አላህ ከታሪኩ ብዙ በተረከልን ነበር። ነገር ግን ከእርሷ በኋላ ከምንም ነገር ብትጠይቅህ አትጉዳኘ አለ» ብለዋል።

**ከዋሻው ምዕራፍ ከአንቀፅ (27-82) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን ቁርኣን በጥሞና የማያነቡትና በህይወታቸው ላይ የማይተገብሩት ክፍሎች በዚህ ዓለምም ሆነ በሚቀጥለው ዓለም የሚያጋጥሟቸው ከፍተኛ ኪሣራ እንደሚጠብቃቸው፤
2. ከአኼራ ሰዎች ጋር መቀመጥና ከእነርሱ ጋር ብዙ ጊዜ ማሳለፍ ከዱንያ ሰዎች አቅም በፈቀደልን ያህል መራቅ፤
3. ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርጉ ሁሉ ግዴታቸው እውነትን መናገር ሲሆን መቀበልና አለመቀበልን ለአላህ መተው እንደሚገባን፤
4. የአማኞችን ምንዳን፤ የከሓዲያን ቅጣት በማውሳት የሰው ልጆችን ማስፈራራት አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
5. የእሳት ቅጣት አስከፊ መሆኑ የጀነት ደስታ ደግሞ ከደስታዎች ሁሉ በላይ እንደሆነ፤
6. አስተምህሮትን ከህዝብ ዘንድ ለማስረፅ ምሳሌዎችን መጥቀስ ተገቢ መሆኑ።
7. ስለ ተዐምርና የወይን ዛፎች ችግኝ አተካከል የተሻለውን መንገድ መጠቆም።
8. የሙቶ መነሳትን እውነትነት ማረጋገጥ፤ ኩራትና እብሪተኝነት ወደ ሽርክ ስለሚደርሱ በሚገባ ማውገዝ፤
9. እንደ ቢላል አል-ሀበሺ የመሰሉ አማኞችና እንደ አቡ ጀህል የመሰሉ ከሓዲያን መጨረሻ ምን እንደሚመስል መተንበይ፤
10. አንድ ነገር ያስደሰተው ሰው ማሻአላህ ላሀውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ ማለቱ እንደሚወደድና ይህም የተባለለት ሰው በአላህ ፈቃድ መጥፎ ነገር እንደማያጋጥመው፤
11. አላህ የባሮቹን ልመና እንደሚቀበል፤
12. በትክክል የተዋረደና ክብሩን ያጣ ማለት በአላህ የተዋረደ መሆኑን፤
13. ትክከለኛ ወዳጅነት ማለት ከአላህ ጋር የሚደረጉ ወዳጅነቶች መሆኑን
14. የሰው ልጅ በትንሳኤ እለት ያለ ምንም ነገር እንደሚቀሰቀስ፤
15. በዱንያ ላይ ሳለን የምንተገብራቸው ነገሮች ሁሉ ተፅፈው ለእያንዳንዳችን በስራ መዘገባችን እንደሚቀርብልን፤
16. አላህ ማንንም የማይበድልና ለማንም ብሎ ግፍን የማይፈፅም መሆኑን፤
17. ዲያቢሎስ ከነዘሮቹ ለአደምና ለዘሮቹ ግልፅ ጠላት መሆኑን፤
18. የአደም ልጆች ለሰይጣን እንዴት እንደሚታዘዙ፤
19. ከአላህ በስተቀር የሚመለክ ማንም እንደሌለ፤
20. የቂያማ ዕለት ከሓዲያን የሚጠብቃቸው አስከፊ ውርደት፤
21. አላህ ለሰዎች ለጥፋታቸው የሚያ ቀርቡት ምክንያቶችን ሁሉ እንደጨረሰባቸው፤
22. የመከራከር ፍላጎት የሰዎች የተፈጥሮ ችግራቸው ስለመሆኑ፤
23. የነብያት መላክ በኸይር ማብሰርና ከመጥፎ ማስጠንቀቅ ብቻ እንጂ ማስገደድ አለመሆኑ፤
24. በቁርኣን ተመክሮ የማይታዘዝና በጥፋቱ ላይ የሚቀጥል ሰው ያለበት ጥፋት ክብደት ምን እንደሚመስል፤
25. ትምህርትን ለመፈለግ መጓዝ እንደሚገባ፤
26. አዋቂዎችም ቢሆኑ እውቀት ሊያዳብሩ እንደሚገባ፤
27. ለጉዞ ስንቅ መያዝ ከተወኩል ጋር እንደማይጋጭና ተገቢ እንደሆነ
28. ተማሪ ለአስተማሪ አስተማሪው ከእሱ የሚያንስ ቢሆንም መተናነስ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
29. አላህ ነብዩ ሙሳን በእውቀት ከሳቸው በላይ ሌላ ሰው መኖሩን ማሳወቁ፤

30. በየትኛውም ጉዞ ላይ ጓደኛ አስፈላጊ እንደሆነ፤
31. ተማሪ አስተማሪውን ማገልገል ተገቢ መሆኑን፤
32. የሰው ልጅ የቱንም ያህል መልካም ቢሆንም ሊረሳ እንደሚችል፤
33. ስህተትን ማረም መልካም ነገርና ተገቢ መሆኑን፤
34. በአሳው ታሪክ ውስጥ የአላህ ሀያልነትና ግልፅ ተአምር መታየቱ፤
35. ለጓደኝነት ቅድሚያ መስፈርት ማስቀመጥ እንደሚቻል፡
36. ባህር ላይ መርከቦችን መሳፈር እንደሚቻል፤
37. መጥፎን ነገር ያወቀ ማውገዝ እንደሚገባ፤
38. በሰዎች ላይ በኢስላም ጫና ማድረግ እንደማይገባ፤
39. በኢስላም የቁሳቁስ ህግ መደንገጉን፤
40. የሰው ልጅ አንዱ ለሌላው የገባውን ቃል ኪዳን ማክበርና መሙላት ግዴታው መሆኑን፤
41. መስተንግዶ የሚገባቸውን ማስተናገድ ተገቢ መሆኑን፤
42. ማንንም ኸይር ሥራ በመተግበር ኸይር መዋል ተገቢ መሆኑን፤
43. የአላህ ቀደር አሚን ብሎ መቀበል እንደሚገባ፤
44. የአላህ ቅንብርና አስተናብሮ እንዴት ያማረና እንዴት መልካም እንደሆነ፤
45. የአባቶች መስተካከል ለልጆች መስተካከል ዋና ምክንያት እንደሆነ፤
46. ብዙውን ገንዘብ ለማዳን የተወሰነውን ማጥፋት እንደሚቻል፤
47. በኢስላም ለማንኛውም የረሳ ሰው እንደማይቀጣበት፤
48. በኢስላም ቁጣ ክልክል መሆኑን፤
49. በቂ ያልሆነ ሀብት ከድህነት እንደማያወጣ፤
50. ለሰሩበት ክፍያ መጠየቅ ክልክል እንዳልሆነ፤
51. መልካም ነገርን መስራት ከመጥፎ ሰዎች ጋርም ቢሆን ተገቢ መሆኑን፤
52. መንገደኛ ማደሪያ ምግብ መጠየቅ እንደሚፈቀድለት፤
53. ልጅ በአባቱ መልካም ስራ እንደሚጠበቅ፤
54. ሁለት ችግሮች ሲጋጩ አነስተኛ ጉዳት ያለውን ማስቀደም እንዳለብን፤
55. ኸድር የሠሩት ነገር ሁሉ በወህይ ከአላህ የታዘዙ እንደነበር እንማራለን።

وَيَسۡـَٔلُونَكَ عَن ذِي ٱلۡقَرۡنَيۡنِۖ قُلۡ سَأَتۡلُواْ عَلَيۡكُم مِّنۡهُ ذِكۡرًا ﴿٨٣﴾ إِنَّا مَكَّنَّا لَهُۥ فِي ٱلۡأَرۡضِ
وَءَاتَيۡنَٰهُ مِن كُلِّ شَيۡءٖ سَبَبٗا ﴿٨٤﴾

**83-84.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስለ ዙልቀርነይንም[*1] ይጠይቁሀል።[*2] በእናንተ ላይ ከእርሱ ወሬን አነባለሁ በላቸው። እኛ እርሱን በምድር ላይ አስመቸነው። በነገሩም ሁሉ መዳረሻ መንገድን ሰጠነው።

✶1 ዐለምን ከገዙ እውቅ አራት ሰዎች አንዱ የነበረና በግብፅ ሀገር ታሪካዊነቱን አሌክሳንደሪያን ከተማ ለመጀመሪያ ጊዜ የቆረቆራት እስከንደር ኢኢብኑ ፊሊቦስ ጃፓናዊ ነው የሚሉ የተፍሲር ምሁራን አሉ። ሆኖም ይህ ሰው የአርት ተማሪ የነበረ እንጂ አማኝ እንዳልነበረ ስለሚታወቅ ከዚህ ታሪክ ጋር አይጣጣምም ተብሏል። ሌሎች ደግሞ ሐምራዊው አቡከርብ እየተባለ ይጠራ የነበረ ሰው ነው ብለዋል።

✶2 እነኚህ ጠያቂዎች አይሁዶች ናቸው።

فَأَتْبَعَ سَبَبًا ﴿٨٥﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا بَلَغَ مَغْرِبَ ٱلشَّمْسِ وَجَدَهَا تَغْرُبُ فِى عَيْنٍ حَمِئَةٍ وَوَجَدَ
عِندَهَا قَوْمًا ۗ قُلْنَا يَٰذَا ٱلْقَرْنَيْنِ إِمَّآ أَن تُعَذِّبَ وَإِمَّآ أَن تَتَّخِذَ فِيهِمْ حُسْنًا ﴿٨٦﴾ قَالَ أَمَّا مَن
ظَلَمَ فَسَوْفَ نُعَذِّبُهُۥ ثُمَّ يُرَدُّ إِلَىٰ رَبِّهِۦ فَيُعَذِّبُهُۥ عَذَابًا نُّكْرًا ﴿٨٧﴾ وَأَمَّا مَنْ ءَامَنَ وَعَمِلَ
صَٰلِحًا فَلَهُۥ جَزَآءً ٱلْحُسْنَىٰ ۖ وَسَنَقُولُ لَهُۥ مِنْ أَمْرِنَا يُسْرًا ﴿٨٨﴾

**85-88.** መንገድንም (ወደ ምዕራብ) ተከተለ። ወደ ፀሐይ መግቢያም በደረሰ ጊዜ ጥቁር ጭቃማ ምንጭ ውስጥ ስትጠልቅ አገኛት*። በአጠገቧም ህዝቦችን አገኘ። ዙልቀርነይን ሆይ፣ ወይም በመግደል ትቀጣለህ ወይም በእነርሱ መልካም ነገርን መማረክን ትሠራለህ አልነው። የበደለውን ሰውማ ወደፊት እንቀጣዋለን ከዚያ ወደ ጌታው ይመለሳል። ብርቱንም ቅጣት ይቀጣዋል አለ። ያመነና መልካምን ሥራ የሰራ ሰው ለእርሱ ከምንዳ በኩል መልካሚቱ ገነት አለችው። ለእርሱም ከትዕዛዛችን ገርን ነገር እናዘዋለን አለ።

* በስተምዕራብ በኩል ያለውን የየብስ ቦታ ጨርሶ ባህሩ አጠገብ ሲደርስ በጥቁር ጭቃማ ውሃ ውስጥ የምትጠልቅ መስላ አያት።

ከዋሻው ምዕራፍ (83) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- እኒህ ጠያቂዎች እኒያ በቀጥታ ወይም በመኮች አማካኝነት ነብዩን ያስጠየቁ አይሁዶች ነበሩ። (ዋሒዲ እና ኢብኑል-ጀውዚ)።

ثُمَّ أَتْبَعَ سَبَبًا ﴿٨٩﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا بَلَغَ مَطْلِعَ ٱلشَّمْسِ وَجَدَهَا تَطْلُعُ عَلَىٰ قَوْمٍ لَّمْ نَجْعَل لَّهُم مِّن
دُونِهَا سِتْرًا ﴿٩٠﴾ كَذَٰلِكَ ۖ وَقَدْ أَحَطْنَا بِمَا لَدَيْهِ خُبْرًا ﴿٩١﴾

**89-91.** ከዚያ መንገድን (ወደ ምስራቅ) ቀጠለ። ወደ ፀሐይ መውጫ በደረሰም ጊዜ ለእነርሱ ከበታቿ መከለያን ባላደረግንላቸው ህዝቦች ላይ ስትወጣ አገኛት። ነገሩ እንደዚሁ ነው። እርሱም ዘንድ ባለው ነገር ሁሉ በእርግጥ በእውቀት ከበብን።

ثُمَّ أَتْبَعَ سَبَبًا ﴿٩٢﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا بَلَغَ بَيْنَ ٱلسَّدَّيْنِ وَجَدَ مِن دُونِهِمَا قَوْمًا لَّا يَكَادُونَ
يَفْقَهُونَ قَوْلًا ﴿٩٣﴾

**92-93.** ከዚያ (ወደ ሰሜን አቅጣጫ) መንገድን ቀጠለ። በሁለቱ ጋራዎችም መካከል በደረሰ ጊዜ በአቅራቢያቸው ንግግርን ለማወቅ የማይቃረቡ ህዝቦችን አገኘ።

قَالُواْ يَٰذَا ٱلْقَرْنَيْنِ إِنَّ يَأْجُوجَ وَمَأْجُوجَ مُفْسِدُونَ فِي ٱلْأَرْضِ فَهَلْ نَجْعَلُ لَكَ خَرْجًا
عَلَىٰٓ أَن تَجْعَلَ بَيْنَنَا وَبَيْنَهُمْ سَدًّا ﴿٩٤﴾ قَالَ مَا مَكَّنِّي فِيهِ رَبِّي خَيْرٌ فَأَعِينُونِي بِقُوَّةٍ أَجْعَلْ
بَيْنَكُمْ وَبَيْنَهُمْ رَدْمًا ﴿٩٥﴾ ءَاتُونِي زُبَرَ ٱلْحَدِيدِ حَتَّىٰٓ إِذَا سَاوَىٰ بَيْنَ ٱلصَّدَفَيْنِ قَالَ ٱنفُخُواْ
حَتَّىٰٓ إِذَا جَعَلَهُۥ نَارًا قَالَ ءَاتُونِيٓ أُفْرِغْ عَلَيْهِ قِطْرًا ﴿٩٦﴾ فَمَا ٱسْطَٰعُوٓاْ أَن يَظْهَرُوهُ وَمَا
ٱسْتَطَٰعُواْ لَهُۥ نَقْبًا ﴿٩٧﴾ قَالَ هَٰذَا رَحْمَةٌ مِّن رَّبِّي فَإِذَا جَآءَ وَعْدُ رَبِّي جَعَلَهُۥ دَكَّآءَ وَكَانَ
وَعْدُ رَبِّي حَقًّا ﴿٩٨﴾

**94-98.** ዙልቀርነይን ሆይ፣ የዕጁጅና መዕጁጅ*1 በምድር ላይ አበላሾች ናቸውና በእኛና በእነርሱ መካከል ግድብን ታደርግልን ዘንድ ግብርን (እናድርግልህን?) አሉ። ጌታዬ በእርሱ ያስመቸብኝ ሀብት ከናንተ ግብር በላጭ ነው። እናም በጉልበት ብቻ አገዙኝ። በእናንተና በእነርሱ መካከል ብርቱን ግድብ አደርጋለሁና አለ። የብረትን ታላላቅ ቁራጮች ስጡኝ አላቸው። በሁለቱ ኮረብታዎች (ጫፍ) መካከልም ባስተካከለ ጊዜ አናፉ አላቸው። ብረቱን እሳትም ባደረገው ጊዜ የቀለጠውን ነሀስ ስጡኝ በእርሱ ላይ አፈስበታለሁና አላቸው። የእጁጅና መዕጁጅ*2 ይህን መከላከያ ሊወጡት አልቻሉም። ለእርሱ መሸንቆርንም እንኳን አልቻሉም። ይህ ግድብ ከጌታዬ ችሮታዎች ነው። የጌታዬ ቀጠሮ በመጣ ጊዜ እንኩትኩት ያደርገዋል። የጌታዬም ቀጠሮ የተረጋገጠ ነው አለ።

*1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዘይነብ ቢንቱ ጃሕሽ እንዳስተላለፉት ከዕለታት አንድ ቀን የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተደናግጠው እንዲህ እያሉ ወደ ቤት ገቡ፡- «ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም። ከዚህ ከተቃረበው ተንኮል ዐረቦች ወዬላቸው። በአመልካችና በአውራ ጣቶቻቸው የክብ ምልክት እያሳዩ ዛሬ የጉግ ማንጉግ (የዕጁጅና መእጁጅ) ግድብ እንዲህ ተከፍቷል። ዘይነብ ኢብኑቱ ጀሕሽ እንዲህ ብላለች«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በእኛ መካከል መልካሞች እያሉ እኛ እንጠፋለን?» ስል ጠየቅኳቸው። እሳቸውም «አዎን! የመጥፎ ሰዎች ቁጥር ከበረከተ» አሉኝ ብሏል።

*2 የእጁጅና መእጁጅ የተባሉ ህዝቦች ከአደም ዝርያወች ሰዎች ናቸው። ስለ እነሱ አካል ሁኔታ የሚወራው፤ ስለ ጥቁረታቸው ስለ ማጠራቸው ስለ ጆሮዎቻቸው ስፋትና ሌላም ሌላም ምንም ዓይነት ማስረጃ የለም። በሰዎች ላይ ችግርና ስቃይ እንደሚያደርሱ በሙስነዱ አህመድ የተዘገበው ሀዲስ ያስረዳል። ማንም ሰው ስለ እነሱ ሁኔታ በሰፊው መረዳት ይኖርበታል። ካልቻለም አዋቂዎችን መጠየቅ ይኖርበታል። አንዳንድ ዘመናዊ ፀሐፊዎች «የእጁጅና መእጁድ የሚባል ነገር የለም» ይላሉ። ሌሎችም «የእጁጅና መእጁጅ ማለት በቴክኖሎጂ ያደጉት ከሓዲያን ሁሉ ማለት» ነው ይላሉ። ለዚህ አባባላቸው የሚያቀርቡት ምክንያት «ዛሬ በምድር ያልተደረሰበት ቦታ የለም። ሆኖም የእነርሱ ቦታ አልተገኘም» ይላሉ። ሆኖም የሰው ልጆች ስላልደረሱበት አላህ «አለ» ያለውን «የለም» ማለት አያስችልም። ስንትና ስንት ነገሮች የቀደምት ሰዎች ሳያገኙት ቀስ በቀስ እየተገኘ ነው። ስለዚህ አላህ ሁሉንም ነገር ጊዜው ሲደርስ ለሕዝቦቹ ይገልጻል።

۞وَتَرَكۡنَا بَعۡضَهُمۡ يَوۡمَئِذٖ يَمُوجُ فِي بَعۡضٖۖ وَنُفِخَ فِي ٱلصُّورِ فَجَمَعۡنَٰهُمۡ جَمۡعٗا ٩٩

**99.** በዚያን ቀን ከፊላቸውን በከፊሉ የሚቀላቀሉ አድርገን እንተዋቸዋለን። በቀንዱም ይነፋል። መሰብሰብንም እንሰበስባቸዋለን።

وَعَرَضۡنَا جَهَنَّمَ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡكَٰفِرِينَ عَرۡضًا ١٠٠ ٱلَّذِينَ كَانَتۡ أَعۡيُنُهُمۡ فِي غِطَآءٍ عَن ذِكۡرِي
وَكَانُواْ لَا يَسۡتَطِيعُونَ سَمۡعًا ١٠١ أَفَحَسِبَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَن يَتَّخِذُواْ عِبَادِي مِن دُونِيٓ
أَوۡلِيَآءَۚ إِنَّآ أَعۡتَدۡنَا جَهَنَّمَ لِلۡكَٰفِرِينَ نُزُلٗا ١٠٢

**100-102.** ገሀነምንም በዚያ ቀን ለከሓዲያን በጣም ማቅረብን እናቀርባታለን። ለእነዚያ አይኖቻቸው ከግሳጼዬ በሽፋን ውስጥ ለነበሩትና መስማትንም የማይችሉ ለነበሩት እናቀርባታለን። እነዚያ በእኔ የካዱት ባሮቼን ከኔ ሌላ አማልዕክት አድርገው መያዛቸውን የማያስቆጣኝ አድርገው አሰቡን? እኛ ገሀነምን ለከሓዲያን መስተንግዶ አዘጋጅተናል።

قُلۡ هَلۡ نُنَبِّئُكُم بِٱلۡأَخۡسَرِينَ أَعۡمَٰلًا ١٠٣ ٱلَّذِينَ ضَلَّ سَعۡيُهُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ
يَحۡسَبُونَ أَنَّهُمۡ يُحۡسِنُونَ صُنۡعًا ١٠٤ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمۡ وَلِقَآئِهِۦ فَحَبِطَتۡ
أَعۡمَٰلُهُمۡ فَلَا نُقِيمُ لَهُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ وَزۡنٗا ١٠٥ ذَٰلِكَ جَزَآؤُهُمۡ جَهَنَّمُ بِمَا كَفَرُواْ وَٱتَّخَذُوٓاْ
ءَايَٰتِي وَرُسُلِي هُزُوًا ١٠٦

**103-106.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሥራዎች በጣም ከሳሪዎቹን እንንገራችሁን? በላቸው። እነዚያ እነርሱ ሥራን* የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ህይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው። እነዚያ እነርሱ በጌታቸው ማስረጃዎችና በመገናኘቱ የካዱት ናቸው ሥራዎቻቸውም ተበላሹ። ለእነርሱም በትንሳኤ ቀን (ጠቃሚ) ሚዛንን አናቆምላቸውም። ነገሩ ይህ ነው። በክህደታቸው አንቀፆቼንና መልዕክተኞቼንም መሳለቂያ አድርገው በመያዛቸው ፍዳቸው ገሀነም ነው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ማንም ሰው በጉዳያችን ላይ በኢስላም ከርሱ ያልሆነ አዲስ ነገር ካመጣ አዲሱ ነገር ውድቅ ነው።»

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ كَانَتۡ لَهُمۡ جَنَّٰتُ ٱلۡفِرۡدَوۡسِ نُزُلًا ١٠٧
خَٰلِدِينَ فِيهَا لَا يَبۡغُونَ عَنۡهَا حِوَلٗا ١٠٨

**107-108.** እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ፊርደውስ* የተባለው የገነት ክፍል ለእነርሱ መስፈሪያ ናቸው። በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ከእርሷ መዛወርን የማይፈልጉ ሲሆኑ መስፈሪያቸው ነው።

* አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ:- «በጀነት ውስጥ መቶ ደረጃዎች ይገኛሉ። በያንዳንዳቸው መካከል በሰማይና በምድር መካከል እንዳለው እርቀት ነው። ፊርደውስ ከፍተኛው ነው። ከበላዩ አርሽ ይሆናል። ከእሱም አራቱ የጀነት ወንዞች ይፈልቃሉ (ይመነጫሉ)። እናም አላህን ስትለምኑ ፊርደውስን ለምኑት» ብለዋል።

قُل لَّوۡ كَانَ ٱلۡبَحۡرُ مِدَادٗا لِّكَلِمَٰتِ رَبِّي لَنَفِدَ ٱلۡبَحۡرُ قَبۡلَ أَن تَنفَدَ كَلِمَٰتُ رَبِّي وَلَوۡ جِئۡنَا بِمِثۡلِهِۦ مَدَدٗا ﴿١٠٩﴾

**109.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባህሩ ለጌታዬ ቃላት መጻፊያ ቀለሞችን ቢሆን ኖሮ ብጤውን ጭማሪ ብናመጣም እንኳ የጌታዬ ቃላት ከማለቋ በፊት ባህሩ ባለቀ ነበር በላቸው።

ከዋሻው ምዕራፍ (109) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በሌሊት ጉዞው ምዕራፍ. (85) ኛው አንቀፅ (ከእውቀትም ጥቂትን እንጂ አልተሰጣችሁም በላቸው) የሚለው ሲወርድ እንዴት ተውራትን ተሰጥተን እንዲህ እንባላለን ሲሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ቁርጡቢ እና ኢብኑል-ጀውዚ።

قُلۡ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡ يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ فَمَن كَانَ يَرۡجُواْ لِقَآءَ رَبِّهِۦ فَلۡيَعۡمَلۡ عَمَلٗا صَٰلِحٗا وَلَا يُشۡرِكۡ بِعِبَادَةِ رَبِّهِۦٓ أَحَدَۢا ﴿١١٠﴾

**110.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነኝ የሚል መልዕክት ወደ እኔ የሚወረድልኝ መሰላችሁ ሰው ነኝ። እናም ከጌታው ጋር መገናኘት የሚፈልግ ሰው ሁሉ መልካም ሥራን ይሥራ።* በጌታውም መገዛት ላይ አንድንም አያጋራ በላቸው።

* መልካም ስራ ማለት ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል:- አላህ ውጫዊ ቅርፅና ውበታችሁን አይመለከትም። ልቦናችሁን ነው የሚመለከተው»

ከዋሻው ምዕራፍ (110) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ጁንደብ ኢብኑ ዙሀይር የተባለ ሰው ወደ ነብዩ መጥቶ«ስራዎችን ለአላህ ነው የምሰራው ነገር ግን ሰው ሲያውቅልኝ ደስ ይለኛል» ብሎ ሲጠይቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ቁርጡቢ።
አንድ ሰው ወደ ነብዩ መጥቶ ጂሃድ እወዳለሁ ነገር ግን ክብሬም እንዲታወቅልኝ እመኛለሁ ስላላቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

**ከዋሻው ምዕራፍ ከአንቀፅ (83-110) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት በግልፅ ማረጋገጥ፤
2. ሰርቶ ክፍያን መጠየቅ ያለና ተገቢ መሆኑን፤

3. የጉልበት አስተዋፅኦ የማድረግን ተገቢነት፤
4. በኸይር ነገር ላይ መተባበር አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
5. ያዕጁጅና ማዕጁጅ የሚባሉ ህዝቦች እንዳሉና የነሱ መከሰት ከቂያማ ቀን ምልክቶች አንዱ መሆኑን፤
6. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
7. መልአክን፤ ጋኔን፤ ወልይንና ሌላንም ፍጡር ወደ አላህ ያቃርቡናል በሚል እነሱን የሚማጸን ሁሉ ወደ ሽርክ እንደሚገባ፤
8. የስሜት ተገዢዎች ሁሉ የተሳሳቱና የጠፉ መሆኑን፤
9. የአላህን ህግና የነቢዩ ተግባር ሁሉ ተቀባይነት እንዳለው፤
10. የሙቶ መነሳትን ሀቅነትና እውነትነት፤
11. ከጀነቶች ሁሉ የሚበልጠው ፊርደውስ የተባለው የጀነት ክፍል መሆኑን፤
12. የአላህ እውቀት ከእውቀቶች ሁሉ የበላይና የማያበቃ መሆኑን፤
13. አላህ የመናገር ባህሪ እንዳለው፤
14. ነብዩ (ﷺ) ሰው እንደሆኑ፤
15. ሽርክን በጥብቅ ማውገዝ፤
16. ለይዩልኝና ለይስሙልኝ መሥራት ከሽርክ ተግባራት አንዱ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የዋሻው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (19)
# የመርየም ምዕራፍ
## (ሱረቱ መርየም)

سُورَةُ مَرْيَمَ

### የወረደው በመካ ነው። የ አናቅፅ ብዛት (98) ናቸው።
### የሱረቱ መርየም መግቢያ

ምዕራፉ ሱረቱል መርየምና ሱረቱል ካፍ፤ ሃ፤ ያ፤ ዓይን፤ ሷድ፤ በመባልም ይታወቃል። ይህ ምዕራፍ ዘጠና ስምንት አናቅፅ ይዞ በመካ ነው የወረደው። የነብዩ ያህያን አወላለድ ታሪክና አባታቸው ዘከሪያ ከሸመገሉ በኋላ ከሚስታቸው መውለድ መመኘታቸውን ያወሳል። ከዚያ በመቀጠል የድንግል መርየምን ታሪክና ነብዩ ዒሳን እንዴት እንደወለደች፤ የነብዩ ኢብራሂምን ታሪክና ከእሳቸውም ልጆች ከኢስማኤልና ኢስሀቅ ዘሮች ስለ ተላኩ ነብያትን፤ ከዚያ በኋላ ሰዎች አማኝና አመፀኛ በመሆን የሚከፋፈሉ መሆናቸውን፤ ጀነት የአማኞች፤ እሳት የአመፀኞች ምንዳ መሆናቸውን ከተነተነ በኋላ ከሓዲያን በገሀነም ውስጥ ሊኖራቸው የሚችለውን ባህሪ ይጠቁማል። አላህ ልጅ አለው የሚሉ ከሓዲያን አስከፊ ክህደት አውስቶ የቁርኣንን ትልቅነት በማንሳት ከሓዲያንን አስጠንቅቆ ነብያትን ያስተባበሉ ከሓዲያን ሁሉ ያለምንም ታሪክ እንደሚጠፉ በማረጋገጥ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

كٓهيعٓصٓ ١

**1.** ካፍ፤ ሃ፤ ያ፤ ዓይን፤ ሷድ፤*

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

ذِكۡرُ رَحۡمَتِ رَبِّكَ عَبۡدَهُۥ زَكَرِيَّآ ٢ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥ نِدَآءً خَفِيّٗا ٣ قَالَ رَبِّ إِنِّي وَهَنَ
ٱلۡعَظۡمُ مِنِّي وَٱشۡتَعَلَ ٱلرَّأۡسُ شَيۡبٗا وَلَمۡ أَكُنۢ بِدُعَآئِكَ رَبِّ شَقِيّٗا ٤ وَإِنِّي خِفۡتُ ٱلۡمَوَٰلِيَ
مِن وَرَآءِي وَكَانَتِ ٱمۡرَأَتِي عَاقِرٗا فَهَبۡ لِي مِن لَّدُنكَ وَلِيّٗا ٥ يَرِثُنِي وَيَرِثُ مِنۡ ءَالِ
يَعۡقُوبَۖ وَٱجۡعَلۡهُ رَبِّ رَضِيّٗا ٦

**2-6.** ይህ ምእራፍ ጌታህ ባርያውን ዘከሪያን በችሮታው ያወሳበት ምእራፍ ነው። ጌታው የሚስጢርን ጥሪ በተጣራ ጊዜ የሆነውን (አስታውስ)። ጌታዬ ሆይ፣ እኔ አጥንቴ ደከመ። ራሴም በሽበት ተንቀለቀለ ጌታዬ ሆይ! አንተንም በመለመኔ፣ ምንጊዜም ዕድለ ቢስ እልሆንኩም አለ። እኔም ከበኋላዬ ከሞትኩ በኋላ ዘመዶቼን (ከእምነት እንዳይወጡ) ፈራሁ። ሚስቴም መካን ነበረች። ስለዚህ ከአንተ ዘንድ ለእኔ ልጅን ስጠኝ። የሚወርሰኝ ከየዕቁብ ቤተሰቦች የእምነትን ሃላፊነት* የሚወርስን ልጅ ስጠኝ። ጌታዬ ሆይ፣ ተወዳጅም አድርገው አለ።

* ይህን ለማለት የተገደድኩት ነብያት የእውቀት እንጂ የገንዘብ ውርስ ስለሌላቸው ነው። ነብዩ (ﷺ) «እኛ ነብያት አንወረስም» ብለዋል።

يَٰزَكَرِيَّآ إِنَّا نُبَشِّرُكَ بِغُلَٰمٍ ٱسۡمُهُۥ يَحۡيَىٰ لَمۡ نَجۡعَل لَّهُۥ مِن قَبۡلُ سَمِيّٗا ٧ قَالَ رَبِّ أَنَّىٰ
يَكُونُ لِي غُلَٰمٞ وَكَانَتِ ٱمۡرَأَتِي عَاقِرٗا وَقَدۡ بَلَغۡتُ مِنَ ٱلۡكِبَرِ عِتِيّٗا ٨ قَالَ كَذَٰلِكَ قَالَ
رَبُّكَ هُوَ عَلَيَّ هَيِّنٞ وَقَدۡ خَلَقۡتُكَ مِن قَبۡلُ وَلَمۡ تَكُ شَيۡـٔٗا ٩

**7-9.** ዘከሪያ ሆይ፣ እኛ ስሙ የሕያ በሆነና ከዚያ በፊት ሞክሼን ባላደረግንለት ወንድ ልጅ እናበስርሃለን አለው። ጌታዬ ሆይ፣ ሚስቴ መካን የነበረች ስትሆን እኔም ከእርጅና የተነሳ ድርቀትን የደረስኩ ስሆን እንዴት ልጅ ይኖረኛል?

(ጅብሪል) አለ ነገሩ እንደዚሁ ነው ጌታህ ከአሁን በፊት ምንም ያልነበርከውን የፈጠርኩህ ስሆን እርሱ በእኔ ላይ ቀላል ነው ብሏል አለ።

قَالَ رَبِّ ٱجۡعَل لِّيٓ ءَايَةٗۖ قَالَ ءَايَتُكَ أَلَّا تُكَلِّمَ ٱلنَّاسَ ثَلَٰثَ لَيَالٖ سَوِيّٗا ١٠ فَخَرَجَ عَلَىٰ قَوۡمِهِۦ مِنَ ٱلۡمِحۡرَابِ فَأَوۡحَىٰٓ إِلَيۡهِمۡ أَن سَبِّحُواْ بُكۡرَةٗ وَعَشِيّٗا ١١

**10-11.** እርሱም ጌታዬ ሆይ፣ እንግዲያውስ ለእኔ ምልክት አድርግልኝ አለ። ምልክትህ ጤናማ ሆነህ ሳለህ ሶስት ሌሊትና (ከነቀናቸው) ሰዎችን ማነጋገር አለመቻልህ ነው አለው። እርሱም ከምኩራቡ ወደ ህዝቦች ወጣ። ጧትና ማታ ጌታችሁን አውሱ አጥሩት በማለትም ወደ እነርሱ ጠቀሰ።

يَٰيَحۡيَىٰ خُذِ ٱلۡكِتَٰبَ بِقُوَّةٖۖ وَءَاتَيۡنَٰهُ ٱلۡحُكۡمَ صَبِيّٗا ١٢ وَحَنَانٗا مِّن لَّدُنَّا وَزَكَوٰةٗۖ وَكَانَ تَقِيّٗا ١٣ وَبَرَّۢا بِوَٰلِدَيۡهِ وَلَمۡ يَكُن جَبَّارًا عَصِيّٗا ١٤ وَسَلَٰمٌ عَلَيۡهِ يَوۡمَ وُلِدَ وَيَوۡمَ يَمُوتُ وَيَوۡمَ يُبۡعَثُ حَيّٗا ١٥

**12-15.** የሕያ ሆይ፣ መጽሐፉን በጥብቅ ያዝ አልነው። ጥበብንም በሕጻንነቱ ሰጠነው። ከእኛም የሆነን ርህራሄ ንፅህናንም (ሰጠነው)። ጥንቁቅም ነበር። ለወላጆችም በጎ ሠሪ ነበር። ትዕቢተኛና አመፀኛም አልነበረም። በተወለደበት ቀንና በሚሞትበት ቀን ህያው ሆኖ በሚነሳበትም ቀን ሰላም በእሱ ላይ ይሁን (ይስፈን)።

وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ مَرۡيَمَ إِذِ ٱنتَبَذَتۡ مِنۡ أَهۡلِهَا مَكَانٗا شَرۡقِيّٗا ١٦ فَٱتَّخَذَتۡ مِن دُونِهِمۡ حِجَابٗا فَأَرۡسَلۡنَآ إِلَيۡهَا رُوحَنَا فَتَمَثَّلَ لَهَا بَشَرٗا سَوِيّٗا ١٧ قَالَتۡ إِنِّيٓ أَعُوذُ بِٱلرَّحۡمَٰنِ مِنكَ إِن كُنتَ تَقِيّٗا ١٨ قَالَ إِنَّمَآ أَنَا۠ رَسُولُ رَبِّكِ لِأَهَبَ لَكِ غُلَٰمٗا زَكِيّٗا ١٩ قَالَتۡ أَنَّىٰ يَكُونُ لِي غُلَٰمٞ وَلَمۡ يَمۡسَسۡنِي بَشَرٞ وَلَمۡ أَكُ بَغِيّٗا ٢٠ قَالَ كَذَٰلِكِ قَالَ رَبُّكِ هُوَ عَلَيَّ هَيِّنٞۖ وَلِنَجۡعَلَهُۥٓ ءَايَةٗ لِّلنَّاسِ وَرَحۡمَةٗ مِّنَّاۚ وَكَانَ أَمۡرٗا مَّقۡضِيّٗا ٢١

**16-21.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መርየም ከቤተሰቧ ወደ ምስራቃዊ ስፍራ በተለየች ጊዜ የሆነውን ታሪኳን በመጽሐፉ ውስጥ አውሳ። ከእነርሱም መጋረጃን አደረገች። መንፈሳችንንም (መልዐኩ ጂብሪልን) ወደ እርሷ ላክን። ለእርሷም ትክክለኛ ሰው ተመሰለላት። ከአንተ በአልረህማን እጠበቃለሁ። ጌታህን ፈሪ ከሆንክ (አትቅረበኝ) አለች። እኔ ንፁሕ የሆነን ልጅ ላንቺ ልሰጥ

የመጣሁ የጌታሽ መልዕክተኛ ነኝ አላት። (በጋብቻ) አንድም ሰው ያልነካኝ ሆኜ አመንዝራ ዝሙተኛ ሳልሆን ለእኔ እንዴት ልጅ ይኖረኛል! አለች። ነገሩ ልክ እንደዚሁ ነው የሚፈፀመው። ጌታሽ እርሱ በእኔ ላይ ገር ነው። ለሰዎችም ተዐምር ከእኛም ችሮታ ልናደርገው (ይህንን ሰራን) ነገሩ የተወሰነም ነው ብሏል አለ።

۞ فَحَمَلَتْهُ فَٱنتَبَذَتْ بِهِۦ مَكَانًا قَصِيًّا ﴿٢٢﴾ فَأَجَآءَهَا ٱلْمَخَاضُ إِلَىٰ جِذْعِ ٱلنَّخْلَةِ قَالَتْ يَٰلَيْتَنِى مِتُّ قَبْلَ هَٰذَا وَكُنتُ نَسْيًا مَّنسِيًّا ﴿٢٣﴾ فَنَادَىٰهَا مِن تَحْتِهَآ أَلَّا تَحْزَنِى قَدْ جَعَلَ رَبُّكِ تَحْتَكِ سَرِيًّا ﴿٢٤﴾ وَهُزِّىٓ إِلَيْكِ بِجِذْعِ ٱلنَّخْلَةِ تُسَٰقِطْ عَلَيْكِ رُطَبًا جَنِيًّا ﴿٢٥﴾ فَكُلِى وَٱشْرَبِى وَقَرِّى عَيْنًا ۖ فَإِمَّا تَرَيِنَّ مِنَ ٱلْبَشَرِ أَحَدًا فَقُولِىٓ إِنِّى نَذَرْتُ لِلرَّحْمَٰنِ صَوْمًا فَلَنْ أُكَلِّمَ ٱلْيَوْمَ إِنسِيًّا ﴿٢٦﴾

**22-26.** ወዲያውኑም አረገዘችው። እርሱንም በሆድዋ ይዛው ወደ ሩቅ ስፍራ ገለል አለች። ምጡ ወደ ዘንባባይቱ ግንድ አስጠጋት። እርሷም ወይኔ! ምነው ከዚህ በፊት በሞትኩና የተረሳሁ በሆንኩ አለች። ልጇ ዒሳም ከበታቿ እንዲህ ሲል ጠራት።* አትዘኚ። ጌታሽ ከበታችሽ ትንሽን ወንዝ በእርግጥ አድርጓልና። የዘምባባይቱን ግንድ ወደ አንቺ ወዝውዢው። በአንቺ ላይ የበሰለን የተምር እሸት ያረግፍልሻልና። ብይ፣ ጠጭም። ተደሰችም ከሰዎች አንድን ነገር ብታይ እኔ ለአዛኙ አምላክ ዝምታን ፆምን ተስያለሁ። እናም ዛሬ ማንንም ሰው በፍፁም አላነጋግርም በይ አላት።

✷ ብዙዎች ይህን ጥሪ ያደርገው መላኩ ጂብሪል ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ራሱ ሕፃኑ ዒሳ ነው ይላሉ።

**ከመርየም ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-26) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የነብዩ ዘከሪያን ታሪክ መዘገብና የነብዩን ነብይነት ማረጋገጥ፤
2. ዱዓን በሚስጥር ማድረግ እንደሚወደድ፤
3. በተፈጥሮ አንዳንድ ሴቶች ላይ መሀንነት እንዳለና የአላህ ችሎታ ግን ከምክንያቶች ሁሉ በላይ ስለ መሆኑና ከፈለገም ምክንያቶቹን ሁሉ በማቋረጥ በመደምሰስ ያለ ምንም ምክንያት ማድረግ እንደሚችል፤
4. ነብያት ገንዘብ እንደማያወርሱና የሚያወርሱት ነገር ቢኖር እውቀትንና ጥበብን እንደሆነ፤
5. ምክንያቶችን መፈለግና መተግበር እምነትን እንደማይነካ፤
6. ለአንድ ነገር ምልክት መስጠት የተፈቀደ ስለመሆኑ፤
7. ዘከርያ መናገር ባቆመበት ጊዜ ሰዎች ያለምንም ቅድመ ስልጠና በምልክት ማወቃቸው፤
8. ጠዋትና ማታ አላህን ማወደስ ያለውን ምንዳ፤

9. ቁርኣንን በማንበብም ሆነ በመረዳት እንዲሁም በመመሪያዎቹ በመስራት አጥብቀን መያዝ እንዳለብን፤
10. በህፃንነት ቁርኣንን የሀፈዘ ትጋትና ጥበብ የተሰጠው መሆኑን፤
11. ለወላጆቹና ጠቅላላ ለሕዝቡ መልካም መዋል ተገቢ ስለ መሆኑ፤
12. የመርየምን ትልቅነትና በጌታዋ ዘንድ የነበራትን ከፍተኛ ክብር፤
13. ጨዋነትና የአይናፍርነት ክብር፤
14. መልአክቶች አላህ በፈደላቸው ዓይነት መቀያየር እንደሚችሉ፤
15. ከሚያስፈሩ ነገሮች ሁሉ መጠበቅ በአላህ ብቻ ስለመሆኑ፤
16. አላህን ፍራቻ በሰዎች ላይም ሆነ በሌላ ክፉን ከማድረስ የሚከለክል ስለመሆኑ፤
17. የነብዩ ዒሳ አፈጣጠር የአላህን ኃይል በግልፅ የሚያሳይ ተዐምር መሆኑን፤
18. ተዓምሮች መካከል መርየም ነቢዩ ዒሳን ያለ አባት አርግዛ መውለዷ።
19. የአላህ ወዳጆች ልዩ ክብርን እንዳላቸው ማረጋገጥ፤
20. የሰው ልጆች የለመዱትን ምክንያት ማሳየት፤
21. ስለት በኢስላም የተፈቀደ ስለመሆኑ እንማራለን።

فَأَتَتۡ بِهِۦ قَوۡمَهَا تَحۡمِلُهُۥۖ قَالُواْ يَٰمَرۡيَمُ لَقَدۡ جِئۡتِ شَيۡـٔٗا فَرِيّٗا ٢٧ يَٰٓأُخۡتَ هَٰرُونَ مَا كَانَ
أَبُوكِ ٱمۡرَأَ سَوۡءٖ وَمَا كَانَتۡ أُمُّكِ بَغِيّٗا ٢٨ فَأَشَارَتۡ إِلَيۡهِۖ قَالُواْ كَيۡفَ نُكَلِّمُ مَن كَانَ فِي
ٱلۡمَهۡدِ صَبِيّٗا ٢٩ قَالَ إِنِّي عَبۡدُ ٱللَّهِ ءَاتَىٰنِيَ ٱلۡكِتَٰبَ وَجَعَلَنِي نَبِيّٗا ٣٠ وَجَعَلَنِي مُبَارَكًا أَيۡنَ
مَا كُنتُ وَأَوۡصَٰنِي بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱلزَّكَوٰةِ مَا دُمۡتُ حَيّٗا ٣١ وَبَرَّۢا بِوَٰلِدَتِي وَلَمۡ يَجۡعَلۡنِي جَبَّارٗا
شَقِيّٗا ٣٢ وَٱلسَّلَٰمُ عَلَيَّ يَوۡمَ وُلِدتُّ وَيَوۡمَ أَمُوتُ وَيَوۡمَ أُبۡعَثُ حَيّٗا ٣٣

**27-33.** እርሱን ተሸክማው ወደ ዘመዶቿ መጣች። መርየም ሆይ፣ ከባድ ነገርን ሠራሽ ፈፀምሽ አሏት። አንቺ የሃሩን* እህት ሆይ! አባትሽ መጥፎ ሰው አልነበረም። እናትሽም አመንዝራ ዝሙተኛ አልነበረችም አሏት። እርሷም ወደ ህፃኑ አመለከተች። እነርሱም በአንቀልባ ያለን ህፃን እንዴት እናናግራለን አሉ። ህፃኑም እኔ የአላህ አገልጋይ ነኝ፤ መጽሐፍን ሰጥቶኛል። ነብይም አድርጎኛል አለ። በየትም ስፍራ ብሆን የተባረኩኝ አድርጎኛል። በህይወትም እስካለሁ በመስገድ ዘካን በመስጠት አዞኛል። ለእናቴም ታዛዥ አድርጎኛል። ትዕቢተኛ እምቢተኛ አላደረገኝም። በተወለድሁበት ቀን በምሞትበት ቀንና ሕያው ሆኜ በምቀሰቀስበትም ቀን ሰላም በእኔ ላይ ይስፈን አለ።

* አንዳንድ የተፍሲር ምሁራን እንዳሉት በዚያ ዘመን ሃሩን የተባለ አንድ ትልቅ ሰው ነበር። በሰዎች ዘንድ የነበረው ክብርና ማዕረግ ይህ ነው የማይባል ነበር። ከቶውንም በሞተ ዕለት ሬሳውን ለመሸኘት ከተገኘው ሕዝብ መካካል አርባ ሺህ ሰዎች በዚሁ ስም የሚጠሩ እንደተገኙ አውስቷል። እና ይህ ሃሩን የግድ የሙሳ ወንድም ነው ማለት ምንም ማስረጃ የለም።

ذَٰلِكَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَۚ قَوۡلَ ٱلۡحَقِّ ٱلَّذِي فِيهِ يَمۡتَرُونَ ﴿٣٤﴾

**34.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ የመርየም ልጅ ዒሳ ታሪክ ነው፤ ያ፣ በእርሱ የሚጠራጠሩበት እውነተኛ ቃል ይህ ነው።

مَا كَانَ لِلَّهِ أَن يَتَّخِذَ مِن وَلَدٍۖ سُبۡحَٰنَهُۥٓۚ إِذَا قَضَىٰٓ أَمۡرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٣٥﴾ وَإِنَّ ٱللَّهَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ﴿٣٦﴾

**35-36.** ለአላህ ልጅን መያዝ አይገባውም። ከጉድለት ሁሉ ጠራ። አንድን ነገር በወሰነ ጊዜ ለእርሱ የሚለው ሁን ብቻ ነው። ወዲያውም ይሆናልና። ዒሳ ለህዝቦቹ አላህ የእኔም ጌታዬ የእናንተም ጌታችሁ ነውና ተገዙት። ይህ ቀጥተኛው መንገድ ነው አለ።

فَٱخۡتَلَفَ ٱلۡأَحۡزَابُ مِنۢ بَيۡنِهِمۡۖ فَوَيۡلٞ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن مَّشۡهَدِ يَوۡمٍ عَظِيمٍ ﴿٣٧﴾ أَسۡمِعۡ بِهِمۡ وَأَبۡصِرۡ يَوۡمَ يَأۡتُونَنَا لَٰكِنِ ٱلظَّٰلِمُونَ ٱلۡيَوۡمَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ﴿٣٨﴾ وَأَنذِرۡهُمۡ يَوۡمَ ٱلۡحَسۡرَةِ إِذۡ قُضِيَ ٱلۡأَمۡرُ وَهُمۡ فِي غَفۡلَةٖ وَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ﴿٣٩﴾ إِنَّا نَحۡنُ نَرِثُ ٱلۡأَرۡضَ وَمَنۡ عَلَيۡهَا وَإِلَيۡنَا يُرۡجَعُونَ ﴿٤٠﴾

**37-40.** ከመካከላቸውም አንጃዎች አህዛቦች አህዛቦች አህዛቦች በእርሱ ነገር ላይ ተለያዩ።*1 ለእነዚያም ለካዱት ሰዎች ከታላቁ ቀን መጋፈጥ ክስተት ወዮላቸው። ወደ እኛ በሚመጡ ቀን ምን ያህል ሰሚ ምን ያህል ተመልካች አደረጋቸው። ግን አመፀኞች በዳዮች ዛሬ በዚህች ዓለም በግልጽ ስህተትና ጥመት ውስጥ ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሚፈረድበት ጊዜ የቁጭትን ቀን አስፈራራቸው እነርሱ አሁን በመዘንጋት ላይ ናቸው። እነርሱ አያምኑምና።*2 እኛ ምድርንና በእርሷም ላይ ያለውን ፍጡር ሁሉ እኛ እንወርሳለን። ወደ እኛም ይመለሳሉ።

*1 ክርስቲያኖችም እንዲሁ በሳቸው ጉዳይ ላይ ከፍተኛ ልዩነቶች አድርገዋል። ነሰጡሪያዎች የተባሉ ቡድኖች «ዒሳ የአላህ ልጅ ነው» ሲሉ፤ መለኪያዎች ደግሞ «ከሶስት ሀይላት አንዱ ነው» ብለዋል። ከሁሉም የባሱ የዕቁባዊያን ደግሞ«ዒሳ እራሱ አላህ ነው» ብለዋል።

*1 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒድ አል. ኹድሪይ እንዳስተላፉት እንዲህ ብለዋል፦ «የትንሳኤ ቀን ሞት ጥቁርና ነጭ በሆነ ሙክት በግ ተመስሎ ይመጣል። ተጣሪው «የጀነት ሰዎች ሆይ!» ብሎ ይጣራል። እነሱም አንገታቸውን እያንጠራሩ ሁኔታውን ይመለከታሉ። «ይህን ታውቁታላችሁን?» ይባላሉ። «አዎን! ይህ ሞት ነው» ይላሉ። ሁሉም በእርግጥ ተመልከተውታል። ተጣሪው በድጋሚ «የጀሀነም ሰዎች ሆይ!» ብሎ ይጣራል። እነርሱም አንገታቸውን እያንጠራሩ ሁኔታውን ይመለከታሉ። «ይህን ታውቁታላችሁን?» ይባላሉ። «አዎን! ይህ ሞት ነው» ይላሉ። ሁሉም በእርግጥ ተመልከተውታል። ከዚያ በኋላ ይታረዳል። «የጀነት ሰዎች

*ሆይ! ሞት የሌለበት የዘልዓለም ሕይወት አላችሁ» እናንተም «የጀሀነም ሰዎች ሆይ! ሞት የሌለበት የዘልዓለም ሕይወት አላችሁ»ይባላል» ከዚያ በኋላ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) የሚከተለውን የቁርኣን አንቀፅ አነበቡ፡- «እነርሱም በዝንጋቴ ላይ ሆነው ሳሉ ....» (መርየም፡ 39)*

وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ إِبۡرَٰهِيمَۚ إِنَّهُۥ كَانَ صِدِّيقٗا نَّبِيًّا ﴿٤١﴾

**41.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመጽሐፉ ውስጥ ኢብራሂምን አውሳ። እርሱ በጣም እውነተኛ ነብይ ነበርና።

إِذۡ قَالَ لِأَبِيهِ يَٰٓأَبَتِ لِمَ تَعۡبُدُ مَا لَا يَسۡمَعُ وَلَا يُبۡصِرُ وَلَا يُغۡنِي عَنكَ شَيۡـٔٗا ﴿٤٢﴾ يَٰٓأَبَتِ
إِنِّي قَدۡ جَآءَنِي مِنَ ٱلۡعِلۡمِ مَا لَمۡ يَأۡتِكَ فَٱتَّبِعۡنِيٓ أَهۡدِكَ صِرَٰطٗا سَوِيّٗا ﴿٤٣﴾ يَٰٓأَبَتِ لَا تَعۡبُدِ
ٱلشَّيۡطَٰنَۖ إِنَّ ٱلشَّيۡطَٰنَ كَانَ لِلرَّحۡمَٰنِ عَصِيّٗا ﴿٤٤﴾ يَٰٓأَبَتِ إِنِّيٓ أَخَافُ أَن يَمَسَّكَ عَذَابٞ
مِّنَ ٱلرَّحۡمَٰنِ فَتَكُونَ لِلشَّيۡطَٰنِ وَلِيّٗا ﴿٤٥﴾ قَالَ أَرَاغِبٌ أَنتَ عَنۡ ءَالِهَتِي يَٰٓإِبۡرَٰهِيمُۖ لَئِن لَّمۡ
تَنتَهِ لَأَرۡجُمَنَّكَۖ وَٱهۡجُرۡنِي مَلِيّٗا ﴿٤٦﴾ قَالَ سَلَٰمٌ عَلَيۡكَۖ سَأَسۡتَغۡفِرُ لَكَ رَبِّيٓۖ إِنَّهُۥ كَانَ بِي
حَفِيّٗا ﴿٤٧﴾ وَأَعۡتَزِلُكُمۡ وَمَا تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَأَدۡعُواْ رَبِّي عَسَىٰٓ أَلَّآ أَكُونَ بِدُعَآءِ
رَبِّي شَقِيّٗا ﴿٤٨﴾ فَلَمَّا ٱعۡتَزَلَهُمۡ وَمَا يَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَهَبۡنَا لَهُۥٓ إِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَۖ وَكُلّٗا
جَعَلۡنَا نَبِيّٗا ﴿٤٩﴾ وَوَهَبۡنَا لَهُم مِّن رَّحۡمَتِنَا وَجَعَلۡنَا لَهُمۡ لِسَانَ صِدۡقٍ عَلِيّٗا ﴿٥٠﴾

**42-50.** ለአባቱ አባቴ ሆይ፣ የማይሰማንና የማያይን ለአንተም ምንንም የማይጠቅምህን (የማይፈይድህን) ጣኦት ለምን ታመልካለህ? ባለው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። አባቴ ሆይ! እኔ ከውቀት ያልመጣልህ ነገር በእርግጥ መጥቶልኛልና ተከተለኝ። ቀጥተኛውን መንገድ እመራሃለሁና። አባቴ ሆይ! ሰይጣንን አትገዛ \አታምልክ\። ሰይጣን ለአልረህማን አመፀኛ ነውና። አባቴ ሆይ! እኔ የአልረህማን ቅጣት ሊያገኝህ እና ከዚያ የሰይጣን ጓደኛ ልትሆን እፈራለሁ። አባቱም ኢብራሂም ሆይ! አንተ አምላኮቼን ትተህ የምትዞር ነህን። ከዚህ ተግባርህ ባትከለከል በእርግጥ እወግርሃለሁ። ረዥም ጊዜንም ተወኝ አለ። ኢብራሂምም ደህና ሁን (ሰላም ለአንተ ይሁን)። ከጌታዬ ምህረትን እለምንልሃለሁ። እርሱ ለእኔ በጣም ሩህሩህ ነውና አለ። ኢብራሂምም እናንተንና ከአላህ ሌላ የምትገዙትን ሁሉ እርቃለሁ። ጌታዬንም ብቻ እገዛለሁ፤ ጌታዬን በመገዛት የማፍር አለመሆኔን እከጅላለሁ (ተስፋ አደርጋለሁ) አለ። እነርሱንና ከአላህ ሌላ የሚገዙትን በራቀ ጊዜ ለእርሱ ኢስሐቅንና የዕቁብን ሰጠነው። ሁለቱንም ነብይ አደረግናቸው። ለእነርሱም ከችሮታችን ሰጠናቸው። ለእነርሱም ከፍ ያለ ምስጉን ዝናን አደረግንላቸው።

**ከመርየም ምዕራፍ ከአንቀፅ (27-50) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የነብዩን ሙሃመድ (ﷺ) ነብይነትና የነቢዩ ዒሳን ነብይነት እንዲሁም የአላህን ነቢያቶች አገልጋይመሆናቸውን ማረጋገጥ፤
2. ነብዩ ዒሳ በልጅነታቸው የመናገራቸውን ተዐምር፤
3. ወላጆችን ማስደሰትና ለእነሱ በጎ መዋል፤
4. ኩራትና ትዕቢት ራስን ከፍ ከፍ ማድረግ የተወገዘ ተግባር መሆኑን፤
5. አይሁዶችም ሆኑ ክርስቲያኖች እንደሚሉት ሳይሆን ነብዩ ዒሳ የአላህ አገልጋይና መልዕክተኛ መሆኑን፤
6. አላህ ልጅ አለው ማለት ከውሸት ሁሉ የከበደ ውሸት ስለመሆኑ፤
7. ተውሒድን ከነብዩ ዒሳ አፍ መማር፤
8. ክርስቲያኖች በዒሳ ጉዳይ ያላቸውን ክርክር መጠቆም፤
9. ለቂያም ቀን ፀፀት ዋና ምክንያት በአላህ መካድና በእርሱ ማጋራት ስለመሆኑ፤
10. ተውሒድን በነብዩ ዒሳ አፍ መማር፤
11. ተውሒድን ማስተማር፤
12. የኢብራሂምን ትልቅነት ማስታወስ፤
13. ከአላህ ሌላ ያለ ነገር ማምለክ በግልፅ ማሳየት፤
14. ጣኦታትን ማምለክ ማለት ሰይጣንንም መታዘዝ እንደሆነ፤
15. ከአማኝና አማኝ ካልሆነ የሚወጣ አባባል ልዩነቱን በግልጽ ማየት፤
16. የመሰናበት ሰላምታ ተገቢ ስለመሆኑና፤
17. ማኩረፍ ተገቢ ስለመሆኑና ያለመሆኑ ያለው ምንዳ፤
18. ጥሩ ዝና ለዳዕዋ ያለውን አስተዋፅኦ እንማራለን።

وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ مُوسَىٰٓۚ إِنَّهُۥ كَانَ مُخۡلَصٗا وَكَانَ رَسُولٗا نَّبِيّٗا ۝٥١ وَنَٰدَيۡنَٰهُ مِن جَانِبِ
ٱلطُّورِ ٱلۡأَيۡمَنِ وَقَرَّبۡنَٰهُ نَجِيّٗا ۝٥٢ وَوَهَبۡنَا لَهُۥ مِن رَّحۡمَتِنَآ أَخَاهُ هَٰرُونَ نَبِيّٗا ۝٥٣

**51-53.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመጽሐፉ ውስጥ ሙሳን አውሳ። እርሱ ምርጥ ነበርና። መልዕክተኛ ነብይም ነበርና። ከጡር ጋራ በስተቀኝ ጎን በኩልም ጠራነው። በሚስጥር ያነጋገርነውም ሲሆን አቀረብነው። ከችሮታችንም ወንድሙን ሃሩንን ነብይ አደረግነው።

وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ إِسۡمَٰعِيلَۚ إِنَّهُۥ كَانَ صَادِقَ ٱلۡوَعۡدِ وَكَانَ رَسُولٗا نَّبِيّٗا ۝٥٤ وَكَانَ يَأۡمُرُ
أَهۡلَهُۥ بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱلزَّكَوٰةِ وَكَانَ عِندَ رَبِّهِۦ مَرۡضِيّٗا ۝٥٥

**54-55.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመጽሐፉ ኢስማዒልንም አውሳ። እርሱ ቀጠሮን አክባሪ ነበረና፤ መልዕክተኛ ነብይም ነበር። ቤተሰቦቹንም በሶላትና በዘካ ያዝ ነበር። በጌታውም ዘንድ ተወዳጅ ነበር።

وَٱذۡكُرۡ فِي ٱلۡكِتَٰبِ إِدۡرِيسَۚ إِنَّهُۥ كَانَ صِدِّيقٗا نَّبِيّٗا ﴿٥٦﴾ وَرَفَعۡنَٰهُ مَكَانًا عَلِيًّا ﴿٥٧﴾

**56-57.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመጽሐፉ ኢድሪስንም አውሳ። እርሱ እውነተኛ ነብይ ነበርና። ኢድሪስን ወደ ከፍተኛም ስፍራ አነሳነው።

أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ أَنۡعَمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مِّنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ مِن ذُرِّيَّةِ ءَادَمَ وَمِمَّنۡ حَمَلۡنَا مَعَ نُوحٖ
وَمِن ذُرِّيَّةِ إِبۡرَٰهِيمَ وَإِسۡرَٰٓءِيلَ وَمِمَّنۡ هَدَيۡنَا وَٱجۡتَبَيۡنَآۚ إِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُ ٱلرَّحۡمَٰنِ
خَرُّواْۤ سُجَّدٗاۤ وَبُكِيّٗا ۩ ﴿٥٨﴾

**58.** እነዚህ (ዐሥሩ) እነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ ችሮታውን የለገሰላቸው ከነብያት ከአዳም ዘር ከኑሕ ጋር በመርከቢቱ ላይ ከጫንናቸውም ዘሮች ከኢብራሂምና ከኢስራኤልም ዘሮች ከመራናቸውና ከመረጥናቸውም የሆኑት የአልረህማን አንቀፆች በእነርሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ ሰጋጆችና አልቃሾች ሆነው ወደ መሬት ይወድቃሉ (ይደፋሉ)።

۞فَخَلَفَ مِنۢ بَعۡدِهِمۡ خَلۡفٌ أَضَاعُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَٱتَّبَعُواْ ٱلشَّهَوَٰتِۖ فَسَوۡفَ يَلۡقَوۡنَ غَيًّا ﴿٥٩﴾
إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحٗا فَأُوْلَٰٓئِكَ يَدۡخُلُونَ ٱلۡجَنَّةَ وَلَا يُظۡلَمُونَ شَيۡـٔٗا ﴿٦٠﴾
جَنَّٰتِ عَدۡنٍ ٱلَّتِي وَعَدَ ٱلرَّحۡمَٰنُ عِبَادَهُۥ بِٱلۡغَيۡبِۚ إِنَّهُۥ كَانَ وَعۡدُهُۥ مَأۡتِيّٗا ﴿٦١﴾ لَّا يَسۡمَعُونَ
فِيهَا لَغۡوًا إِلَّا سَلَٰمٗاۖ وَلَهُمۡ رِزۡقُهُمۡ فِيهَا بُكۡرَةٗ وَعَشِيّٗا ﴿٦٢﴾ تِلۡكَ ٱلۡجَنَّةُ ٱلَّتِي نُورِثُ مِنۡ
عِبَادِنَا مَن كَانَ تَقِيّٗا ﴿٦٣﴾

**59-63.** ከእነርሱም በኋላ ሶላትን ያጎደሉ (የተው) ከንቱ ፍላጎቶችንም የተከተሉ መጥፎ ትውልዶች ተተኩ። (ገይ የሚባልን) የገሀነምንም ሸለቆ በእርግጥ ያገኛሉ። ግና ከእነርሱ የተፀፀቱ በአላህ ያመኑ በጎንም ስራ የሰሩ ሰዎች ወደ ገነት ይገባሉ። አንዳችንም አይበደሉም። የመኖሪያን ገነቶች ያችን አልረህማን ለባሮቹ በሩቅ ሆነው ሳሉ ተስፋ ቃል የገባላቸውን ይገባሉ። እርሱ ተስፋው ሁልጊዜም ተፈጻሚ ነውና። በእርሷ ሰላምን እንጂ ውድቅን ነገር አይሰሙም። ለእነርሱም በእርሷ ውስጥ ጧትም ማታም ሲሳያቸው አላቸው። ይህ ያቺ ከባሮቻችን ጥንቁቆች ለሆኑት ሁሉ የምናወርሳት ገነት ናት።

**ከመርየም ምዕራፍ ከአንቀፅ (51-63) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የኢኽላስ ዋጋው ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ፤
2. ለአላህ ካሉት ባህሪያቶች መካከል መናገር ስለ መሆኑ፤
3. አላህ ለማንም ያልሰጠውን ለሙሳ ማድረጉ እንማራለን።
4. ይህ ሰው የነቢዩ ኑህ አያትና ለመጀመሪያ ጊዜ በብዕር የፃፉ ናቸው።
5. ነብይነትን ማረጋገጥ ይፋ ማውጣት፤
6. በሶላትና በዘካ ላይ የሚደረጉ ግፊቶች ያላቸው ወደር የለሽ ምንዳ ምን እንደሆነ፤
7. በቃል ማውሳትንና በአንደበትም ሆነ በተግባር እውነተኛት ያለው ከፍተኛ ምንዳ፤
8. መጥፎ ትውልድ አንዳንድ ባህሪያት መጠቆምና ማስጠንቀቅ፤
9. በስሜት ተውጦ ሶላትን እያሳለፉ ከመሞት ማስጠንቀቅ፤
10. የተውበት በር ሁልጊዜ ክፍት ስለ መሆኑ፤
11. የፈሪሃውያኖችን አገር የጀነትን ፀጋዎች መጠቆም፤
12. በጀነት ሰዎችና በእሳት ሰዎች መወራረስ እንዳለ መጠቆም፤
13. ጀነትን የሚወርሱ ፈሪሀውያኖች ሲሆኑ እሳትን ደግሞ አመፀኞች ስለ መሆናቸው እንማራለን።

وَمَا نَتَنَزَّلُ إِلَّا بِأَمۡرِ رَبِّكَۖ لَهُۥ مَا بَيۡنَ أَيۡدِينَا وَمَا خَلۡفَنَا وَمَا بَيۡنَ ذَٰلِكَۚ
وَمَا كَانَ رَبُّكَ نَسِيّٗا ٦٤ رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا فَٱعۡبُدۡهُ وَٱصۡطَبِرۡ لِعِبَٰدَتِهِۦۚ
هَلۡ تَعۡلَمُ لَهُۥ سَمِيّٗا ٦٥

**64-65.** (ጂብሪል ለሙሐመድ) በጌታህ ትእዛዝ እንጂ አንወርድም። በፊታችን፣ በኋላችንና በዚህም መካከል ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። ጌታህ ረሺ አይደለም አለ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱ የሰማያትና የምድር በሁለቱም መካከል ላለው ሁሉ ጌታ ነውና ተገዛው። እርሱን በመገዛትም ላይ ታገሥ። ለእርሱ ሞክሼን ታውቃለህን?

ከመርየም ምዕራፍ (64) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) መልአኩ ጅብሪልን ለምን ከዚህ በበለጠ አትጎበኘንም ብለው ሲጠይቁት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

وَيَقُولُ ٱلۡإِنسَٰنُ أَءِذَا مَا مِتُّ لَسَوۡفَ أُخۡرَجُ حَيًّا ٦٦ أَوَلَا يَذۡكُرُ ٱلۡإِنسَٰنُ أَنَّا خَلَقۡنَٰهُ مِن
قَبۡلُ وَلَمۡ يَكُ شَيۡـٔٗا ٦٧

**66-67.** ሰው በሞትኩ ጊዜ ወደ ፊት ህያው ሆኜ ከመቃብር እወጣለሁን? ይላል። ሰው ከዚህ በፊት ምንም ነገር ያልነበረ ሲሆን እኛ የፈጠርነው መሆኑን አያስታውስምን?*

✷ ከመርየም ምዕራፍ (66) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ኡበይ ኢብኑ ኸለፍ የተባለ አንድ ከሃዲ የበሰበሰ አጥንት ይዞ ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት በእጁ የያዘውን አጥንት እየፈረፈረ «ሙሐመድ እኮ ከሞትን በኋላ እንቀሰቀሳለን አለ። ይህን ብናኝ የሆነውን አጥንት ከየት አምጥቶ ነው የሚቀሰቅሰው» እያለ በማፌዙ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

فَوَرَبِّكَ لَنَحۡشُرَنَّهُمۡ وَٱلشَّيَٰطِينَ ثُمَّ لَنُحۡضِرَنَّهُمۡ حَوۡلَ جَهَنَّمَ جِثِيّٗا ٦٨ ثُمَّ لَنَنزِعَنَّ مِن كُلِّ
شِيعَةٍ أَيُّهُمۡ أَشَدُّ عَلَى ٱلرَّحۡمَٰنِ عِتِيّٗا ٦٩ ثُمَّ لَنَحۡنُ أَعۡلَمُ بِٱلَّذِينَ هُمۡ أَوۡلَىٰ بِهَا صِلِيّٗا ٧٠

**68-70.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በጌታህ እንምላለን ሰይጣናት ጋር በእርግጥ እንሰበስባቸዋለን። ከዚያ በገሀነም ዙሪያ የተንበረከኩ ሆነው እናቀርባቸዋለን። ከዚያ ከየቡድኖቹ ሁሉ ከእነርሱ ያንን በአልረህማን ላይ በድፍረት በጣም ብርቱ የሆነውን መዘን እናወጣለን። ከዚያ እነዚያን በእርሷ ለመቃጠል ተገቢ የሆኑትን ሰዎች እናውቃለን።

وَإِن مِّنكُمۡ إِلَّا وَارِدُهَاۚ كَانَ عَلَىٰ رَبِّكَ حَتۡمٗا مَّقۡضِيّٗا ٧١ ثُمَّ نُنَجِّي ٱلَّذِينَ ٱتَّقَواْ وَّنَذَرُ
ٱلظَّٰلِمِينَ فِيهَا جِثِيّٗا ٧٢

**71-72.** (ሰዎች ሆይ!) ከናንተ መካከል ወደ ገሀነም የማይወርድ✷1 አንድም የለም። መውረዱም ጌታህ የፈረደው ግዴታና አይቀሬ ዉሳኔ ነው።✷2 ከዚያ እነዚያን አላህን የፈሩትን ብቻ እናድናለን። አመፀኞችን ደግሞ የተንበረከኩ ሆነው በውስጧ እንተዋቸዋለን።

✷1 «መውረድ የሚለው ቃል መግባትን ሁልጊዜ አያስከትልም። ስለዚህ ሁሉም ሰው ገሀነም ይገባል ብሎ ለመተርጎም አያደርስም። ምክንያቱም «እነዚያ ከእኛ መልካሟ ቃል ለእነርሱ ያለፈችላቸው እነዚያ ከርሷ የተራቁ ናቸው። የሚል አንቀጽ ስላለ ....» (21/101)

✷2 ሁሉም ቆም ብሎ ሊያነበው የሚገባው አዋጅ ነው። አስፈሪ ነው። አንድ ቀን እንኳን የዚህ ጉዳይ አሳስቦህ ተጨንቀህ ታውቃለህን አሰብበት። ዐብዱላህ ኢብኑ ረዋሀህ ታመው ሳሉ አለቀሱ ምን ሁነው ነው ተብለው ሲጠየቁ «ከእናንተ መካከል ወደ ገሀነም የማይወርድ አንድም የለም» የሚለውን አንቀፅ አስታውሼ ነው አሉ። አቡ መይሰረህ የተባሉ ሰው ሲተኙ ያለቅሱ ነበርና ሲጠየቁ «ከእናንተ መካከል ወደ ገሀነም የማይወርድ አንድም የለም» ማለቱ ተነገረን እንውጣ አንውጣ ግን አናውቅም አሉ።

وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُنَا بَيِّنَٰتٖ قَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَيُّ ٱلۡفَرِيقَيۡنِ خَيۡرٞ
مَّقَامٗا وَأَحۡسَنُ نَدِيّٗا ٧٣ وَكَمۡ أَهۡلَكۡنَا قَبۡلَهُم مِّن قَرۡنٍ هُمۡ أَحۡسَنُ أَثَٰثٗا وَرِءۡيٗا ٧٤ قُلۡ
مَن كَانَ فِي ٱلضَّلَٰلَةِ فَلۡيَمۡدُدۡ لَهُ ٱلرَّحۡمَٰنُ مَدًّاۚ حَتَّىٰٓ إِذَا رَأَوۡاْ مَا يُوعَدُونَ إِمَّا ٱلۡعَذَابَ وَإِمَّا
ٱلسَّاعَةَ فَسَيَعۡلَمُونَ مَنۡ هُوَ شَرّٞ مَّكَانٗا وَأَضۡعَفُ جُندٗا ٧٥

73-75. በእነርሱም ላይ አንቀፆቻችን ግልፅ ማስረጃዎች ሆነው በተነበቡላቸው ጊዜ እነዚያ የካዱት ለእነዚያ ላመኑት ከሁለቱ ክፍሎች መኖሪያው የበለጠውና ሸንጎውም ይበልጥ የሚያምረው ማንኛው ነው ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች እነርሱ በቁሳቁስና በእይታ በጣም ያማሩትን ብዙዎችን አጥፍተናል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በስህተት ውስጥ የሆነ ሰው አዛኙ አምላክ ለእርሱ ጥመትን ይጨምርለት (ማዘግየትን ያዘገየዋል።) የሚዛትባቸውንም ቅጣትን ወይም ሰዓቲቱን ባዩ ጊዜ እርሱ ስፍራው መጥፎና ሰራዊቱ ደካማ ማን እንደሆነ በእርግጥ ያውቃሉ በላቸው።

وَيَزِيدُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ٱهْتَدَوْا۟ هُدًى ۗ وَٱلْبَٰقِيَٰتُ ٱلصَّٰلِحَٰتُ خَيْرٌ عِندَ رَبِّكَ ثَوَابًا وَخَيْرٌ مَّرَدًّا ﴿٧٦﴾

76. እነዚያን የቀኑትን ሰዎች አላህ ቅንነትን ይጨምርላቸዋል። መልካም ቀሪ ስራዎች በጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው። በመመለሻነትም የተሻሉ ናቸው።

أَفَرَءَيْتَ ٱلَّذِى كَفَرَ بِـَٔايَٰتِنَا وَقَالَ لَأُوتَيَنَّ مَالًا وَوَلَدًا ﴿٧٧﴾ أَطَّلَعَ ٱلْغَيْبَ
أَمِ ٱتَّخَذَ عِندَ ٱلرَّحْمَٰنِ عَهْدًا ﴿٧٨﴾ كَلَّا ۚ سَنَكْتُبُ مَا يَقُولُ وَنَمُدُّ لَهُۥ مِنَ ٱلْعَذَابِ مَدًّا ﴿٧٩﴾
وَنَرِثُهُۥ مَا يَقُولُ وَيَأْتِينَا فَرْدًا ﴿٨٠﴾

77-80. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያንን በአንቀፆቻችን የካደውንና በትንሣኤ ቀን ገንዘብም ሆነ ልጅ በእርግጥ እሰጣለሁ ያለውን አየህን? ሩቁን ምስጢር ዐወቀን? ወይስ አዛኙ አምላክ ዘንድ ቃል ኪዳንን ያዘ? ከዚህ አቋሙ ይታቀብ አይሰጠውም። የሚለውን ሁሉ በእርግጥ እንጽፋለን። ለእርሱም ከቅጣት ጭማሬን እንጨምርለታለን። አለኝ የሚለውንም ሁሉ እንወርሰዋለን" ወደ እኛም ብቻውን ሆኖ ይመጣል።

ከመርየም ምዕራፍ (77) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት (አንድ ዓስ ኢብኑ ዋኢል የተባለ ከሃዲ ኸባብ ኢብኑል አረት ከተባለ ሙስሊም የገንዘብ ብድር ነበረበትና እንዲከፍለው ሲጠይቀው «በሙሐመድ ካልካድክ በስተቀር አልሰጥህም» አለው። ኸባብም በጌታዬ ይሁንብኝ ሞተህ እስከምትነሣ ድረስ በሙሐመድ አልክድም» በማለት መለሰለት። ከሃዲውም እንግዲያውስ ሞቼ ስቀሰቀስ ገንዘብም ልጅም ስለሚኖረኝ እዚያው እንገናኝና እዚያው እከፍልሀለሁ»ብሎ በማላገጡ ነው እነህ አናቅፅ የወረዱት (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَٱتَّخَذُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ ءَالِهَةً لِّيَكُونُواْ لَهُمۡ عِزّٗا ٨١ كَلَّاۚ سَيَكۡفُرُونَ بِعِبَادَتِهِمۡ وَيَكُونُونَ
عَلَيۡهِمۡ ضِدًّا ٨٢ أَلَمۡ تَرَ أَنَّآ أَرۡسَلۡنَا ٱلشَّيَٰطِينَ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ تَؤُزُّهُمۡ أَزّٗا ٨٣ فَلَا تَعۡجَلۡ
عَلَيۡهِمۡۖ إِنَّمَا نَعُدُّ لَهُمۡ عَدّٗا ٨٤

**81-84.** ከአላህ ሌላ አማልዕክትን ለእነርሱ መከበሪያ አማላጅ እንዲሆኗቸው ያዙ። ከዚህ ተግባራቸው ይከልከሉ (ይታቀቡ)። መገዛታቸውን በእርግጥ ወደፊት ይክዷቸዋል። በእነርሱም ላይ ተቃራኒ (ባላጋራ) ይሆኑባቸዋል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ሰይጣናትን በከሓዲያን ላይ በመጥፎ ሥራ የሚገፋፏቸው ሲሆኑ የላክንባቸው መሆናችንን አላየህምን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእነርሱ መቀጣት ላይ አትቸኩል። ለእነርሱ ቀንን መቁጠርን እንቆጥርላቸዋለንና።

يَوۡمَ نَحۡشُرُ ٱلۡمُتَّقِينَ إِلَى ٱلرَّحۡمَٰنِ وَفۡدٗا ٨٥ وَنَسُوقُ ٱلۡمُجۡرِمِينَ إِلَىٰ جَهَنَّمَ وِرۡدٗا ٨٦
لَّا يَمۡلِكُونَ ٱلشَّفَٰعَةَ إِلَّا مَنِ ٱتَّخَذَ عِندَ ٱلرَّحۡمَٰنِ عَهۡدٗا ٨٧

**85-87.** አማኞችን የተከበሩ ጭፍሮች ሆነው ወደ አዛኙ አምላክ የምንሰበሰብበትንና ከሓዲያንን የተጠሙ ሆነው ወደገሀነም የምንነዳበትን ቀን (አስታውሱ)። አል ረህማን (አዛኙ አላህ) ዘንድ ቃል ኪዳንን የያዘ ሰው ቢሆን እንጂ ሌሎች ማማለድን አይችሉም።

وَقَالُواْ ٱتَّخَذَ ٱلرَّحۡمَٰنُ وَلَدٗا ٨٨ لَّقَدۡ جِئۡتُمۡ شَيۡـًٔا إِدّٗا ٨٩ تَكَادُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ يَتَفَطَّرۡنَ مِنۡهُ وَتَنشَقُّ
ٱلۡأَرۡضُ وَتَخِرُّ ٱلۡجِبَالُ هَدًّا ٩٠ أَن دَعَوۡاْ لِلرَّحۡمَٰنِ وَلَدٗا ٩١ وَمَا يَنۢبَغِي لِلرَّحۡمَٰنِ أَن يَتَّخِذَ وَلَدًا ٩٢

**88-92.** አጋሪዎች አል ረህማን አላህ ልጅ ወለደ አሉ። (አጋሪዎች ሆይ!) እጅግ ከባድና መጥፎን ነገር በእርግጥ አመጣችሁ። ከዚህ ንግግራቸው ሰማያት ሊቀደዱ፤ ምድርም ልትሰነጠቅ፣ ጋራዎችም ተንደው ሊወድቁ ይቃረባሉ። ይህም ለአል ረህማን (ለአላህ) ልጅ አለው ስለ አሉ ነው። አዛኙ ጌታ ልጅን መያዝ አይገባውም።

إِن كُلُّ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ إِلَّآ ءَاتِي ٱلرَّحۡمَٰنِ عَبۡدٗا ٩٣ لَّقَدۡ أَحۡصَىٰهُمۡ وَعَدَّهُمۡ
عَدّٗا ٩٤ وَكُلُّهُمۡ ءَاتِيهِ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ فَرۡدًا ٩٥ إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ
سَيَجۡعَلُ لَهُمُ ٱلرَّحۡمَٰنُ وُدّٗا ٩٦

**93-96.** በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ በትንሣኤ ቀን (ለአልረህማን) ለአዛኙ ጌታ ባሪያ ሆነው የሚመጡ እንጂ ሌላ አይደሉም። አላህ በእርግጥ በዕውቀቱ ከቧቸዋል። መቁጠርንም ቆጥሯቸዋል። ሁሉም በትንሳኤ ቀን ለየብቻ ሆነው ወደ እርሱ መጪዎች ናቸው። እነዚያ በአላህ ያመኑና በጎ ስራዎችን የሰሩ ለእነርሱ* አልረህማን ውዴታን ይሰጣቸዋል።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ አንድን ሰው ከወደደ ጅብሪልን ይጠራና«አላህ እከሌን ወዷል። ጅብሪል ሆይ! እሱን ውደደው» ይለዋል። ጅብሪልም ይህን ሰው ይወደዋል። ከዚያም ጅብሪል ሰማይ ላይ ላሉ ነዋሪዎች «አላህ እከሌን ወዷልና እናንተም ልትወዱት ይገባል»ይላቸዋል። በሰማይ የሚኖሩ ሁሉ ይወዱታል። በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ደስታም ለዚህ ሰው ይሰጠዋል»

فَإِنَّمَا يَسَّرۡنَٰهُ بِلِسَانِكَ لِتُبَشِّرَ بِهِ ٱلۡمُتَّقِينَ وَتُنذِرَ بِهِۦ قَوۡمٗا لُّدّٗا ٩٧

**97.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምላስህ ቁርአንን ያገራነው በእርሱ ጥንቁቆችን ልታበስርበትና በእርሱም ተከራካሪ ሕዝቦችን ልታስፈራራበት ዘንድ ነው።

وَكَمۡ أَهۡلَكۡنَا قَبۡلَهُم مِّن قَرۡنٍ هَلۡ تُحِسُّ مِنۡهُم مِّنۡ أَحَدٍ أَوۡ تَسۡمَعُ لَهُمۡ رِكۡزَۢا ٩٨

**98.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች ብዙ ትውልዶችን አጥፍተናል። ከእነርሱ አንድን እንኳ ታያለህን ወይንስ ለእነርሱ ሹክሹክታን ትሰማለህን?

**ከመርየም ምዕራፍ ከአንቀፅ (64-98) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህ ሙሉ ስልጣንና የተሟላ እውቀት ማረጋገጥ፤
2. አላህ በፍፁም እንደማይረሳ በግልፅ ማስተማር፤
3. አላህ የአለማት ጌታ መሆኑን አረጋግጦ በብቸኝነት ተመላኪ መሆኑንም ማስተማር፤
4. አላህን ማምለኩ ግዴታ ስለመሆኑና በዚህ እምነት ላይ እስከ ዕለተ ሞት ድረስ መፅናቱ ግዴታ ስለመሆኑ፤
5. አላህ ቢጤም ሆነ ተመሳሳይ የሌለው ስለ መሆኑ፤
6. የሙቶ መነሳትን እውነትነት ማረጋገጥ፤
7. በሲራጥ ላይ ማለፍ ትክክለኛ ስለ መሆኑ፤
8. የጥፋት መሪዎችና አቀናባሪዎች ወደ ጀሀነም የሚወርዱበት ከተከታዮቻቸው በፊት ስለ መሆኑ፤
9. ከሃዲ የሚኮራው በሀብቱና በጉልበቱ ሲሆን ሙዕሚን ግን በእምነቱና በስነ ምግባሩ ስለመሆኑ፤
10. አላህ ለግፈኞች ጊዜ የሚሰጥበት ምክንያት ለማስጨበጥና ከማስረጃ ኋላ እንዲጠፉ ስለመሆኑ፤
11. አላህ ግፈኞችን በሚቀጣበት ጊዜም ሆነ ቁርአን በሚሰሙበት አማኞች እምነታቸው እንደሚጨምር፤

12. ከሃዲ በተለይም ገንዘብ ወይም ጉልበት ወይም ስልጣን ካለው ለደህና ለችግረኛ ደንታ እንደሌለው፤
13. ሙቶ መነሳት ሀቅ መሆኑን ማረጋገጥ፤
14. ለከሓዲያን የተዘጋጀው ቅጣት እጥፍ ድርብ ስለመሆኑ፤
15. ፍጡሮች ከግዙፍ እስከ ኢምንት ያሉት በሙሉ የአላህ አገልጋይና ባሪያ ሲሆኑ አላህ በእውቀትም ሆነ በችሎታው አቻ የሌለው ጌታ ነው። በአላህ ላይ መዋሸት ከባድ ሲሆን የቂያማ ቀን ከአላህ ሌላን አካል የሚያመልክ ሁሉ ከአምላኪዎቹ ጋር እንደሚጣል፤
16. በምድር ላይ ለተንኮል የሚያሯሯጡት በሰይጣን እርዳታና ግፊት ነው። እነሱም ከዚህ ተግባራቸውና ግፎች እስካልተቆጠቡ ድረስ ከእነሱ በፊት በነበሩ ግፈኞች ላይ አላህ ያሳረፈውን በትር እንደሚያሳርፋባቸው፤
17. ከእነዚህ በተጨማሪ በአላህ አምነው መልካም ስራ የሚሰሩ ሁሉ አላህ እንደሚወዳቸውና፤ የፈሪሀውያኖችን ትልቅነትና የአመፀኞችን ወራዳነት ከአናቅፅ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የመርየም ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (20)
# የጧሃ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ጧሀ)

سُورَةُ طه

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (135) ናቸው።
### የሱረቱ ጧሃ መግቢያ

የቁርአንን ትልቅነት በመግለፅ ይጀምርና ቁርኣን የወረደው ከሀያሉ ከአላህ መሆኑን ያመለክታል። በማስከተልም ነብዩ ሙሳ እንዴት እንደ ተላኩ፣ ወንድማቸውን ሀሩንን አብሮ እንዲልክላቸው አላህን መጠየቃቸውን፣ ከፊርአውን ጋር እንዴት እንደተከላከሉና ከዚያ ምን እንደተከተላቸው፣ ነብዩ ሙሳና የአረመኔው ንጉስ ፈርኦን ድግምተኞች የተከራከሩበትን እልህ አስጨራሽ ድርድር ያብራራል። ድግምተኞቹ የኢስላምን ትክክለኛነት፣ በተቀበሉ ጊዜ ፈርአውን ምን አይነት ቅጣት ሊቀጣቸው እንደዛተባቸው፣ ከዚያ አላህ ሙሳንና አማኞችን ነፃ አውጥቶ ፈርአውንንና ሰራዊቱን በባህር እንዳሰመጣቸው ይገለፃል። ሙሳ ሰዎቻቸውን ትተው ወደ ጡርሲና ጋራ እንደሄዱና ሙሳ ሳሚሪይ የተባለ ሰው ሕዝቦችን እንዴት እንደፈተናቸውና ሽርክ እንዳስገባቸው፣ ሙሳም ሲመለሱ ተቆጥተው የወንድማቸውን ፀጉር ይዘው መጎተታቸውን ያስታውሳል።

ከዚያ ሳሚሪይ ምን እንደደረሰበትና ከዚህም ታሪክ ምን እንደምንማር፣ የመልዕክትና የትዕግስትን አስፈላጊነት አውስቶ ነብይ የሚላክበት ምክንያት ነብያትን የተቀበሉ አማኞች የሚያገኙትን ደስታና ፌሽታ፣ በአንፃሩም ያመፁ ከሓዲያን የሚጠብቃቸውን ቅጣት በማውሳት ትምህርቱን ያጠቃልላል።

የመጀመሪያ አካባቢ ያሉት አናቅፅ ለታላቁ ሶሐባ ለዑመር መስለም ምክንያት እንደነበረች ብዙ የታሪክ ሰዎች ተስማምተውበታል። የዑመር መስለም ብቻ ሳይሆን የሚገርመው የዚህችን ምዕራፍ መግቢያ እየደጋገሙ «እውነትም ይህን ያለ ጌታ ከእሱ ሌላ ማንም ሊመለክ አይገባውም። በሉ ሙሐመድ ያለበትን አሳዩኝ።» እስከማለት ድረስ። ይህን ጉዳይ ይበልጥ የሚያስገርመው ዑመር በዚያው ዕለት ከቤታቸው ሲወጡ ነብዩን (ﷺ) ለመግደል አስበው የነበሩ መሆናቸው ነው። በዚህም ንግግር (በቁርኣን) ባያምኑ በፍላጎታቸው ላይ በቁጭት ነፍስህን አጥፊ ልትሆን ይፈራልሀል። (18/6) «ሙሐመድ ሆይ! አማኞች ባለመሆናቸው በቁጭት ነፍስህን እንዳታጠፋ ይፈራልሃል (ያሰጋል)፣» (26/3) የዚህ አንቀፅና መሰሎቹ ትርጉምም ሆነ ማብራሪያው በአልአዕራፍ ምዕራፍ ላይ በሰፊው ተዘርዝሯል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

طه ١ مَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡقُرۡءَانَ لِتَشۡقَىٰٓ ٢ إِلَّا تَذۡكِرَةٗ لِّمَن يَخۡشَىٰ ٣ تَنزِيلٗا مِّمَّنۡ
خَلَقَ ٱلۡأَرۡضَ وَٱلسَّمَٰوَٰتِ ٱلۡعُلَى ٤ ٱلرَّحۡمَٰنُ عَلَى ٱلۡعَرۡشِ ٱسۡتَوَىٰ ٥

**1-5.** ጧ፤ ሃ፤* (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህን ለሚፈራ ሰው ሁሉ መገሠጫ ይሆን ዘንድ እንጂ አንድትቸገር ቁርአንን በአንተ ላይ አላወረድንም። ቁርአን ምድርንና የላይኛዎችን\ የተከበሩ\ ሰማያትን ከፈጠረ አምላክ ተወረደ። አል ረህማን (አዛኙ ጌታ) በዐርሹ ላይ ከፍ አለ።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፤ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርአን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

ከጧሃ ምዕራፍ ከ (1-2) ኛ ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አቡ ጀህልና ነድር ቢን ሐሪስ «ሙሐመድ ሆይ! የእኛን እምነት በመተውህ ችግር ደረሰብህ። ጠመምክ። ለፋህ። ለምን አትተወውምና ወደ ነበርክበት አትመለስም» ስላሏቸው ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا وَمَا تَحۡتَ ٱلثَّرَىٰ ٦ وَإِن تَجۡهَرۡ بِٱلۡقَوۡلِ
فَإِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلسِّرَّ وَأَخۡفَى ٧ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ لَهُ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰ ٨

**6-8.** በሰማያት፣ በምድርና በመካከላቸውም ያለው ከዐፈር በታችም ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በንግግር ብትጮህ አላህ ከጩኸቱ የተብቃቃ ነው። እርሱ ምስጢርን ከዚያ በጣም የተደበቀንም ያውቃልና። አላህ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። ለእርሱ መልካሞች የሆኑ ስሞች* አሉት።

* አላህ አያሌ መልካም ስሞች አሉት። በሰፊው በአል. አዕራፍ (180) ኛው ግርጌ ላይ አልፏል።

**ከጧሃ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-8) የምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኢስላማዊ ህግጋት ሊከብዱና ሊያለፉ ይችላሉ የሚለውን ከንቱ አባባል በማስረጃ ማጣጣልና ውሸት መሆኑን ማረጋገጥ፤
2. ስለ ወህይ እና ስለ ሙቶ መነሳት ግልፅ መረጃ መስጠት፤
3. የአላህን ባህሪያቶች ከፍጡር ጋር አለማስመሠል እና መልዕክታቸውንም አለማራቆት (አለ ማሳጣት)፤
4. የአላህን ብቸኛ ጌትነት እና የእርሱን መልካም ስሞችንና ሙሉ ባህሪያቶችን ማፅደቅ እንማራለን።

وَهَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ مُوسَىٰٓ ﴿٩﴾ إِذۡ رَءَا نَارٗا فَقَالَ لِأَهۡلِهِ ٱمۡكُثُوٓاْ إِنِّيٓ ءَانَسۡتُ نَارٗا لَّعَلِّيٓ
ءَاتِيكُم مِّنۡهَا بِقَبَسٍ أَوۡ أَجِدُ عَلَى ٱلنَّارِ هُدٗى ﴿١٠﴾ فَلَمَّآ أَتَىٰهَا نُودِيَ يَٰمُوسَىٰٓ ﴿١١﴾ إِنِّيٓ أَنَا۠
رَبُّكَ فَٱخۡلَعۡ نَعۡلَيۡكَ إِنَّكَ بِٱلۡوَادِ ٱلۡمُقَدَّسِ طُوٗى ﴿١٢﴾ وَأَنَا ٱخۡتَرۡتُكَ فَٱسۡتَمِعۡ لِمَا يُوحَىٰٓ ﴿١٣﴾
إِنَّنِيٓ أَنَا ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدۡنِي وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ لِذِكۡرِيٓ ﴿١٤﴾

**9-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሙሳ ወሬ (ታሪክ) መጥቶሃልን? (ደርሶሃል)። እሳትን ባየና ለቤተሰቦቹ (እዚህ) ቆዩ። እኔ እሳትን አየሁ፤ ከእርሷ ችቦን ላመጣላችሁ ወይም እሳቲቱ ዘንድ መሪን ላገኝ እከጅላለሁ ባለ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። እናም ወደ እርሷ በመጣ ጊዜ ሙሳ ሆይ በማለት ተጠራ። እኔ ጌታህ እኔ ነኝ ጫማዎችህን አውልቅ አንተ በተቀደሰው ሸለቆ በጡዋ ነህና እኔም መረጥኩህ ስለ ሆነም የሚወረድልህን ነገር በደንብ አዳምጥ። እኔ አላህ ነኝ። ያለ እኔ ትክክለኛ አምላክ የለምና እኔን ብቻ ተገዛኝ። ሶላትንም እኔን ለማውሳት ስትል በአግባቡ ስገድ።

إِنَّ ٱلسَّاعَةَ ءَاتِيَةٌ أَكَادُ أُخۡفِيهَا لِتُجۡزَىٰ كُلُّ نَفۡسِۭ بِمَا تَسۡعَىٰ ﴿١٥﴾ فَلَا يَصُدَّنَّكَ عَنۡهَا مَن
لَّا يُؤۡمِنُ بِهَا وَٱتَّبَعَ هَوَىٰهُ فَتَرۡدَىٰ ﴿١٦﴾

**15-16.** ነፍስ ሁሉ በምትሰራው ነገር ትመነዳ ዘንድ ሰዓቲቱ በእርግጥ መጪናት። የትንሳኤውን ወሬ ልደብቃት እቀርባለሁ። (ሙሳ ሆይ)፣ በእርሷ የማያምንና ዝንባሌውን የሚከተል ሰው ሁሉ ከእርሷ አያግድህ ትጠፋለህና።

وَمَا تِلۡكَ بِيَمِينِكَ يَٰمُوسَىٰ ﴿١٧﴾ قَالَ هِيَ عَصَايَ أَتَوَكَّؤُاْ عَلَيۡهَا وَأَهُشُّ بِهَا عَلَىٰ غَنَمِي وَلِيَ
فِيهَا مَـَٔارِبُ أُخۡرَىٰ ﴿١٨﴾ قَالَ أَلۡقِهَا يَٰمُوسَىٰ ﴿١٩﴾ فَأَلۡقَىٰهَا فَإِذَا هِيَ حَيَّةٞ تَسۡعَىٰ ﴿٢٠﴾ قَالَ خُذۡهَا
وَلَا تَخَفۡۖ سَنُعِيدُهَا سِيرَتَهَا ٱلۡأُولَىٰ ﴿٢١﴾ وَٱضۡمُمۡ يَدَكَ إِلَىٰ جَنَاحِكَ تَخۡرُجۡ بَيۡضَآءَ مِنۡ غَيۡرِ
سُوٓءٍ ءَايَةً أُخۡرَىٰ ﴿٢٢﴾ لِنُرِيَكَ مِنۡ ءَايَٰتِنَا ٱلۡكُبۡرَى ﴿٢٣﴾ ٱذۡهَبۡ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ إِنَّهُۥ طَغَىٰ ﴿٢٤﴾

**17-24.** ሙሳ ሆይ፣ ይህች በቀኝ እጅህ ያለችው ምንድ ናት? (ተባለ)። እርሷ በትሬ ናት በእርሷ ላይ እደገፍባታለሁ። በእርሷም ለፍየሎቼ ቅጠልን አረግፍባታለሁ። ለእኔም በእርሷ ሌሎች ጉዳዮችም አሉኝ አለ። አላህም ሙሳ ሆይ፣ እስቲ ጣላት አለው። ሙሳም ጣላትና፤ ወዲያውም እርሷ የምትሮጥ እባብ ሆነች። አላህም ሙሳ ሆይ! ያዛት አትፍራም ወደ መጀመሪያ ጠባይዋ

እንመልሳታለን አለው። እጅህንም ወደብብትህ አስገባ። ሌላ ተዐምር ስትሆን ያለ ምንም ችግር ነጭ ሆና ትወጣለችና። (ሙሳ ሆይ)፣ ከተዐምራቶቻችን ታላቋን እናሳይህ ዘንድ (ይህን ፈፀምን)። (ሙሳ ሆይ)፣ ወደ ፈርዖን ሂድ። እርሱ ወሰን (ድንበር) አልፏልና።

قَالَ رَبِّ ٱشْرَحْ لِى صَدْرِى ﴿٢٥﴾ وَيَسِّرْ لِىٓ أَمْرِى ﴿٢٦﴾ وَٱحْلُلْ عُقْدَةً مِّن لِّسَانِى ﴿٢٧﴾
يَفْقَهُوا۟ قَوْلِى ﴿٢٨﴾ وَٱجْعَل لِّى وَزِيرًا مِّنْ أَهْلِى ﴿٢٩﴾ هَٰرُونَ أَخِى ﴿٣٠﴾ ٱشْدُدْ بِهِۦٓ أَزْرِى ﴿٣١﴾
وَأَشْرِكْهُ فِىٓ أَمْرِى ﴿٣٢﴾ كَىْ نُسَبِّحَكَ كَثِيرًا ﴿٣٣﴾ وَنَذْكُرَكَ كَثِيرًا ﴿٣٤﴾
إِنَّكَ كُنتَ بِنَا بَصِيرًا ﴿٣٥﴾

**25-35.** (ሙሳም) አለ ጌታዬ ሆይ! ልቤን አስፋልኝ። ተልእኮየንም አግራልኝ። የምላሴንም መኮላተፍንም አስወግድልኝ። ንግግሬን ይረዱ ዘንድ። ከቤተሰቦቼም ለእኔ ረዳትን አድርግልኝ። ኃይሌንም በወንድሜን በሃሩን አበርታልኝ። በብዛት እንድናጠራህና በብዛት እንድናወሳህ በነገሬ አጋራው። አንተ በእኛ ነገር ዐዋቂ ነህና።

**ከጧሃ ምዕራፍ አንቀፅ (9-35) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥና በይፋ ማሳወቅ ማወጅ፤
2. ነብያት ሁሉ ወደ ላኢላሀ ኢለሏህ ጥሪ ያደረጉ ስለ መሆናቸው፤
3. መናገር ከአላህ ባህሪያቶች አንዱ ስለ መሆኑ፤
4. አላህ በረካ ያደረገበት ነገር ላይ በረካን መፈለግ ተግቢ ስለመሆኑ፤
5. በኢስላም ሰላት መስገድ ግዴታ ስለመሆኑ፤
6. የቂያማ ቀንን የመደበቁን ጥበብ መጠቆም፤
7. የነብዩን (ﷺ) መልዕክተኝነት ማረጋገጥ፤
8. ያልተናቁ ነገሮችን በቀኝ እጅ መያዝ ተገቢና የበለጠ ነገር ስለመሆኑ፤
9. በየትኛውም ጊዜ ብትር መያዝ ተገቢ ስለመሆኑ፤
10. ፍየል መጠበቅ የነብያት ሱና ስለ መሆኑ፤
11. መሣሪያን ከመጠቀሙ በፊት መለማመድ ተገቢ ስለመሆኑ፤
12. ዘንዷ እባብ መሆንዋ፤ እጃቸው በረዶ መስሎ መቀየሩ ከሙሣ ተአምሮች ዋና ዋናዎቹ መሆናቸውን፤
13. ድንበር ማለፍ ማለት ባሪያ የማይገባውን የአምላክነት ባህሪ መጠየቅ ስለመሆኑ፤
14. በሚያስጨንቅ ነገር ሁሉ ወደ አላህ መጠጋት ግዴታ ስለመሆኑ፤
15. የሠው ልጅ መስራት ለሚፈልገው ሁሉ አስቀድሞ መዘጋጀት አስፈላጊ ስለመሆኑ እንማራለን።

قَالَ قَدۡ أُوتِيتَ سُؤۡلَكَ يَٰمُوسَىٰ ﴿٣٦﴾ وَلَقَدۡ مَنَنَّا عَلَيۡكَ مَرَّةً أُخۡرَىٰٓ ﴿٣٧﴾

**36-37.** አላህ ሙሳ ሆይ! ልመናህ በእርግጥ ተቀባይነትን አገኝቷል አለ። (ሙሳ ሆይ!) በሌላም ጊዜ በአንተ ላይ በእርግጥ ውለታን ውለናል።

إِذۡ أَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ أُمِّكَ مَا يُوحَىٰٓ ﴿٣٨﴾ أَنِ ٱقۡذِفِيهِ فِي ٱلتَّابُوتِ فَٱقۡذِفِيهِ فِي ٱلۡيَمِّ فَلۡيُلۡقِهِ ٱلۡيَمُّ بِٱلسَّاحِلِ يَأۡخُذۡهُ عَدُوّٞ لِّي وَعَدُوّٞ لَّهُۥۚ وَأَلۡقَيۡتُ عَلَيۡكَ مَحَبَّةٗ مِّنِّي وَلِتُصۡنَعَ عَلَىٰ عَيۡنِيٓ ﴿٣٩﴾

**38-39.** ለእናትህ በራእይ ባሳወቅን ጊዜ ነው። ሕፃኑን በሳጥኑ ውስጥ አስገቢው እርሱንም (ሳጥኑን) በባህር ላይ ጣይው ባህሩም በዳርቻው ይጥለዋል (ይተፋዋል)። ለእኔም ለእርሱም ጠላት የሆነ ሰው ይይዘዋልና በማለት (ባሳወቅን ጊዜ ለገስንልህ) ልትወደድና በእኔም ጥበቃ ታድግ ዘንድ በአንተ ላይም ከእኔ የሆነ መወደድን ጣልኩብህ።

إِذۡ تَمۡشِيٓ أُخۡتُكَ فَتَقُولُ هَلۡ أَدُلُّكُمۡ عَلَىٰ مَن يَكۡفُلُهُۥۖ فَرَجَعۡنَٰكَ إِلَىٰٓ أُمِّكَ كَيۡ تَقَرَّ عَيۡنُهَا وَلَا تَحۡزَنَۚ وَقَتَلۡتَ نَفۡسٗا فَنَجَّيۡنَٰكَ مِنَ ٱلۡغَمِّ وَفَتَنَّٰكَ فُتُونٗاۚ فَلَبِثۡتَ سِنِينَ فِيٓ أَهۡلِ مَدۡيَنَ ثُمَّ جِئۡتَ عَلَىٰ قَدَرٖ يَٰمُوسَىٰ ﴿٤٠﴾ وَٱصۡطَنَعۡتُكَ لِنَفۡسِي ﴿٤١﴾

**40-41.** እህትህ በምትሄድና የሚያሳድገውን ሰው ላመላክታችሁን? ባለች ጊዜ (መወደድን ጣልኩብህ)። ወደ እናትህም ዓይኗ እንዲረጋና እርሷ እንዳታዝን መለስንህ። ነፍስንም ገደልክ ከጭንቅም አዳንንህ። ፈተናዎችንም ፈተንህ። በመድየን ቤተሰቦችም ውስጥ ብዙ ዓመታትን ተቀመጥክ። ከዚያ ሙሳ ሆይ! በተወሰነ ጊዜ ላይ መጣህ። ለራሴም ለመልዕክተኝነት መረጥኩህ።

ٱذۡهَبۡ أَنتَ وَأَخُوكَ بِـَٔايَٰتِي وَلَا تَنِيَا فِي ذِكۡرِي ﴿٤٢﴾ ٱذۡهَبَآ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ إِنَّهُۥ طَغَىٰ ﴿٤٣﴾ فَقُولَا لَهُۥ قَوۡلٗا لَّيِّنٗا لَّعَلَّهُۥ يَتَذَكَّرُ أَوۡ يَخۡشَىٰ ﴿٤٤﴾

**42-44.** አንተና ወንድምህ በተዐምራቶቼ ሆናችሁ ሂዱ። እኔን ከማውሳትም አትቦዝኑ። ወደ ፈርዖን ሂዱ። እርሱ ወሰን አልፏልና። እርሱ ምንአልባት ይገሰጥ ወይም ይፈራ ዘንድ። ለእርሱ ለስላሳን ቃል ተናገሩት።

قَالَا رَبَّنَآ إِنَّنَا نَخَافُ أَن يَفۡرُطَ عَلَيۡنَآ أَوۡ أَن يَطۡغَىٰ ﴿٤٥﴾

**45.** ጌታችን ሆይ! እኛ በእኛ ላይ ክፋት በመስራት መቸኮሉን ወይም ኩራትን መጨመሩን እንፈራለን አሉ።

قَالَ لَا تَخَافَآۖ إِنَّنِي مَعَكُمَآ أَسۡمَعُ وَأَرَىٰ ﴿٤٦﴾ فَأۡتِيَاهُ فَقُولَآ إِنَّا رَسُولَا رَبِّكَ فَأَرۡسِلۡ مَعَنَا بَنِيٓ
إِسۡرَٰٓءِيلَ وَلَا تُعَذِّبۡهُمۡۖ قَدۡ جِئۡنَٰكَ بِـَٔايَةٖ مِّن رَّبِّكَۖ وَٱلسَّلَٰمُ عَلَىٰ مَنِ ٱتَّبَعَ ٱلۡهُدَىٰٓ ﴿٤٧﴾ إِنَّا قَدۡ
أُوحِيَ إِلَيۡنَآ أَنَّ ٱلۡعَذَابَ عَلَىٰ مَن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰ ﴿٤٨﴾

**46-48.** አላህም እኔ በእርግጥ ከናንተ ጋር ነኝና አትፍሩ። የሚለውንም ሁሉ እሰማለሁ። አያለሁም አለ። ወደ እርሱም ሂዱና እኛ የጌታህ መልዕክተኞች ነንና የኢስራኤልን ልጆች ሁሉ ከእኛ ጋር ልቀቅ በሉትም። አታሰቃያቸውም። ከጌታህ በሆነው ተዐምር በእርግጥ መጥተንሃልና። ሰላምም ቀጥታን በተከተለ ሰው ሁሉ ላይ ይሁን በሉት። እኛ እነሆ የአላህ ቅጣት እውነትን ባስተባበለና እምቢ ባለ ሰው ላይ እንደሆነ በእርግጥ መልዕክት ተወረደልን።

قَالَ فَمَن رَّبُّكُمَا يَٰمُوسَىٰ ﴿٤٩﴾ قَالَ رَبُّنَا ٱلَّذِيٓ أَعۡطَىٰ كُلَّ شَيۡءٍ خَلۡقَهُۥ ثُمَّ هَدَىٰ ﴿٥٠﴾ قَالَ
فَمَا بَالُ ٱلۡقُرُونِ ٱلۡأُولَىٰ ﴿٥١﴾ قَالَ عِلۡمُهَا عِندَ رَبِّي فِي كِتَٰبٖۖ لَّا يَضِلُّ رَبِّي وَلَا يَنسَى ﴿٥٢﴾
ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ مَهۡدٗا وَسَلَكَ لَكُمۡ فِيهَا سُبُلٗا وَأَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَخۡرَجۡنَا
بِهِۦٓ أَزۡوَٰجٗا مِّن نَّبَاتٖ شَتَّىٰ ﴿٥٣﴾ كُلُواْ وَٱرۡعَوۡاْ أَنۡعَٰمَكُمۡۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّأُوْلِي ٱلنُّهَىٰ ﴿٥٤﴾

**49-54.** ፊርዖንም ሙሳ ሆይ! ጌታችሁ ማነው? አለ። ጌታችን ያ ፍጥረቱን ሁሉ የሚያስፈልገውን ቅርፁንና ባህሪውን የሰጠ ከዚያ ሁሉንም ለተፈጠረለት የመራው ነው አለው። ፊርዖንም የመጀመሪያይቱ ዘመናት ህዝቦች ሁኔታስ ምንድን ነው? አለ። ሙሳ የዚህ ዕውቀት እጌታዬ ዘንድ በመጽሐፍ የተመዘገበ ነው። ጌታዬ አይሳሳትም አይረሳምም አለው። ጌታችን ያ! ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ በእርሷም ውስጥ ለእናንተ መንገድን ያገራላችሁ ውሃንም ከሰማይ ያወረደላችሁ ነው አለ። በእርሱም ከተለያየ በቃይ ዓይነቶችን አወጣንላችሁ። ለራሳችሁ ብሉ። እንስሳዎቻችሁንም አግጡ። (ባዮች ሆነን አወጣንላችሁ)። በዚህ ውስጥ ለአእምሮ ባለቤቶች ሁሉ በእርግጥ ተዐምራት አለበት።

*مِنۡهَا خَلَقۡنَٰكُمۡ وَفِيهَا نُعِيدُكُمۡ وَمِنۡهَا نُخۡرِجُكُمۡ تَارَةً أُخۡرَىٰ ﴿٥٥﴾
وَلَقَدۡ أَرَيۡنَٰهُ ءَايَٰتِنَا كُلَّهَا فَكَذَّبَ وَأَبَىٰ ﴿٥٦﴾

**55-56.** (ሰዎች ሆይ)፣ ከምድር ፈጠርናችሁ። ወደ እርሷም ውስጥ እንመልሳችኋለን። ከእርሷም በሌላ ጊዜ እናወጣችኋለን። ተዐምራቶቻችንንም ሁሏንም ለፈርዖን በእርግጥ አሳየነው። አስተባበለም። እምቢም አለ።

قَالَ أَجِئْتَنَا لِتُخْرِجَنَا مِنْ أَرْضِنَا بِسِحْرِكَ يَٰمُوسَىٰ ﴿٥٧﴾ فَلَنَأْتِيَنَّكَ بِسِحْرٍ مِّثْلِهِۦ فَٱجْعَلْ بَيْنَنَا وَبَيْنَكَ مَوْعِدًا لَّا نُخْلِفُهُۥ نَحْنُ وَلَآ أَنتَ مَكَانًا سُوًى ﴿٥٨﴾ قَالَ مَوْعِدُكُمْ يَوْمُ ٱلزِّينَةِ وَأَن يُحْشَرَ ٱلنَّاسُ ضُحًى ﴿٥٩﴾

**57-59.** ሙሳ ሆይ! ከምድራችን በድግምትህ ልታወጣን መጣህብን አለ። መሰሉንም ድግምት እናመጣብሃለን። በእኛና በአንተም መካከል እኛም አንተም የማንጥሰው የሆነ ቀጠሮን በመካከለኛ ስፍራ አድርግልን አለ። ሙሳ ቀጠሯችሁ ያ፣ የማጌጫው የበአሉ ቀን ነው ሰዎችም ረፋድ ላይ እንዲሰበሰቡ ይሁን አለ።

فَتَوَلَّىٰ فِرْعَوْنُ فَجَمَعَ كَيْدَهُۥ ثُمَّ أَتَىٰ ﴿٦٠﴾ قَالَ لَهُم مُّوسَىٰ وَيْلَكُمْ لَا تَفْتَرُوا۟ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا فَيُسْحِتَكُم بِعَذَابٍ ۖ وَقَدْ خَابَ مَنِ ٱفْتَرَىٰ ﴿٦١﴾

**60-61.** ፈርዖንም ዞረ። ተንኮሉን ሰበሰበ። ከዚያ መጣ። ሙሳ ለእነርሱ አላቸው፤ ወዮላችሁ በአላህ ላይ ውሸትን አትቅጠፉ። በቅጣት ያጠፋችኋልና። የቀጠፈም ሰው በእርግጥ አፈረ አላቸው።

فَتَنَٰزَعُوٓا۟ أَمْرَهُم بَيْنَهُمْ وَأَسَرُّوا۟ ٱلنَّجْوَىٰ ﴿٦٢﴾ قَالُوٓا۟ إِنْ هَٰذَٰنِ لَسَٰحِرَٰنِ يُرِيدَانِ أَن يُخْرِجَاكُم مِّنْ أَرْضِكُم بِسِحْرِهِمَا وَيَذْهَبَا بِطَرِيقَتِكُمُ ٱلْمُثْلَىٰ ﴿٦٣﴾ فَأَجْمِعُوا۟ كَيْدَكُمْ ثُمَّ ٱئْتُوا۟ صَفًّا ۚ وَقَدْ أَفْلَحَ ٱلْيَوْمَ مَنِ ٱسْتَعْلَىٰ ﴿٦٤﴾

**62-64.** ድግምተኞች እርስ በእርስ ተጨቃጨቁ። ሆኖም ውይይቱን ደበቁት። እነዚህ በእርግጥ ደጋሚዎች ናቸው። ከምድራችሁ በድግምታቸው ሊያወጧችሁ በላጪቱንም መንገዳችሁን ሊያስወግዱባችሁ ይሻሉ አሉ። ተንኮላችሁንም አጠንክሩ። ከዚያ ተሰልፋችሁ ኑ። ዛሬ ያሸነፈም ሰው ምኞቱን አገኘ ተባባሉ።

قَالُوا۟ يَٰمُوسَىٰٓ إِمَّآ أَن تُلْقِىَ وَإِمَّآ أَن نَّكُونَ أَوَّلَ مَنْ أَلْقَىٰ ﴿٦٥﴾

**65.** ሙሳ ሆይ! ወይ በመጀመሪያ ትጥላለህ ወይም እኛ እንጣል (ምረጥ) አሉ።

قَالَ بَلۡ أَلۡقُواْۖ فَإِذَا حِبَالُهُمۡ وَعِصِيُّهُمۡ يُخَيَّلُ إِلَيۡهِ مِن سِحۡرِهِمۡ أَنَّهَا تَسۡعَىٰ ٦٦
فَأَوۡجَسَ فِي نَفۡسِهِۦ خِيفَةٗ مُّوسَىٰ ٦٧

**66-67.** ሙሳም እናንተ በመጀመሪያ ጣሉ አላቸው፡፡ ጣሉም፡፡ ወዲያውም ገመዶቻቸውና ዘንጎቻቸው ከድግምታቸው የተነሳ የሚሮጡ እባቦች ሆነው ወደ እነርሱ ተመሰሉበት፡፡ ሙሳም በውስጡ ፍርሃት አደረበት፡፡

قُلۡنَا لَا تَخَفۡ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡأَعۡلَىٰ ٦٨ وَأَلۡقِ مَا فِي يَمِينِكَ تَلۡقَفۡ مَا صَنَعُوٓاْۖ
إِنَّمَا صَنَعُواْ كَيۡدُ سَٰحِرٖۖ وَلَا يُفۡلِحُ ٱلسَّاحِرُ حَيۡثُ أَتَىٰ ٦٩ فَأُلۡقِيَ ٱلسَّحَرَةُ سُجَّدٗا
قَالُوٓاْ ءَامَنَّا بِرَبِّ هَٰرُونَ وَمُوسَىٰ ٧٠

**68-70.** አትፍራ፡፡ የበላዩ አንተ ነህና አልነው፡፡ በቀኝ እጅህ ያለችውን ብትር ጣል፡፡ የሰሩትን ሁሉ ትውጣለችና፡፡ ያ፣ የሰሩት ሁሉ የድግምተኛ ተንኮል ብቻ ነውና፡፡ ድግምተኛም በመጣበት ስፍራ ሁሉ አይቀናውም፡፡ ድግምተኞችም ሱጁድ ወረዱ፡፡ በሃሩንና በሙሳ ጌታ አመንን አሉ፡፡

قَالَ ءَامَنتُمۡ لَهُۥ قَبۡلَ أَنۡ ءَاذَنَ لَكُمۡۖ إِنَّهُۥ لَكَبِيرُكُمُ ٱلَّذِي عَلَّمَكُمُ ٱلسِّحۡرَۖ
فَلَأُقَطِّعَنَّ أَيۡدِيَكُمۡ وَأَرۡجُلَكُم مِّنۡ خِلَٰفٖ وَلَأُصَلِّبَنَّكُمۡ فِي جُذُوعِ ٱلنَّخۡلِ
وَلَتَعۡلَمُنَّ أَيُّنَآ أَشَدُّ عَذَابٗا وَأَبۡقَىٰ ٧١

**71.** ፈርዖንም ለእናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት ለእርሱ አመናችሁለትን፡፡ እርሱ በእርግጥ ያ፣ ድግምትን ያስተማራችሁ መሪያችሁ ነው፡፡ እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን በማናጋት እቆራርጣችኋለሁ፡፡ በዘምባባም ግንዶች ላይ እሰቅላችኋለሁ፡፡ የማንኛችን ቅጣት በጣም ብርቱና የሚቆይ መሆኑን በዚያ ጊዜ ታውቃላችሁ አላቸው፡፡

**ከጧሃ ምዕራፍ ከአንቀፅ (36-71) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን እዝነትና በበጐ ማስተናበሩን ማየት፤
2. አላህ ለአገልጋዩና ለባሪያው ለነብዩ ሙሳ የሠጣቸው ክብር፤
3. አላህ ነብዩ ሙሳን እንደሚወዳቸው ያሳየበት ግልፅ ሂደት፤
4. እነዚህን መሰል ታሪክ በመተረክ የነብዩን ነብይነት ማረጋገጥ፤
5. አላህን በልብም በአንደበትም ሆነ በተግባር ማስታወስ ያለውን ትልቅነት፤
6. ሰዎችን በምናስተምርበት ጊዜ ጥበብን መጠቀም ግዴታ ስለመሆኑ፤

7. አላህ በድጋፍና በድል ከመልካም ባሮቹና ከወዳጆቹ ጋር ስለመሆኑ፤
8. ግፈኛ ሊያመጣ የሚችለውን ችግር በመቻል ከመጥፎ ባህሪው እንዲቆጠብ መግለፅ መምከር ተገቢ ስለመሆኑ
9. የሚያውቁ ሰዎች ለጥያቄዎች ተገቢውን መልስ የመመለስ ግዴታ እንዳለባቸው፤
10. የአንድ ሙስሊም መልካምነት ከሚገለፁባቸው ባህሪያት መካከል በማይመለከተው ጉዳይ አለመግባቱ ነው፤
11. አላህ ከመሣሣት እና ከመርሳት የፀዳ ስለመሆኑ፤
12. ዓለምን በማየት ስለ አላህ መኖርና ብቸኛ አምላክነት መረዳት እንደሚቻል
13. የፊርዓውን ትዕቢትና አምባገነንነት ምን እንደሚመስል መጠቆም፤
14. ድግምት እውነትነት ያለውና ራሱን የቻለ ትምህርት ያለው ስለመሆኑ፤
15. ሀቅን ለማውጣት መጋፈጥ ተገቢ ስለመሆኑ፤
16. ለየትኛውም ትግል አመቺ ጊዜን መምረጡ ተገቢ ስለመሆኑ
17. በአላህ ላይ መዋሸት ከወንጀል ሁሉ አስከፊ ወንጀል ስለመሆኑ፤
18. ከሰው ልጆች ተንኮል አንዱ እምነታዊ ጉዳይን ወደ ፖለቲካ መቀየር ስለመሆኑ፤
19. አንዳንድ ነገሮችን ሲያዩ መደንገጥ መስጋት እምነትን እንደማይነካ፤
20. ድግምተኞች አንዳንድ ነገሮችን የመለዋወጥ ባህሪ የሚያሳዩት በማስመሠል እንጂ እውነትነት ባለው መንገድ እንዳልሆነ፤
21. በኢስላም የድግምት ተግባር ክልክል ስለመሆኑ፤
22. አላህ በሙሣ አማካኝነት ያሳየው ተዓምር በድግምተኞች ላይ ያደረሰው ተፅዕኖ
23. የአማኝን ጀግንነት የትኛውም ማስፈራሪያ እንደማያሸንፈውና እንደማያሸማቅቀው እንማራለን።

قَالُواْ لَن نُّؤۡثِرَكَ عَلَىٰ مَا جَآءَنَا مِنَ ٱلۡبَيِّنَٰتِ وَٱلَّذِي فَطَرَنَاۖ فَٱقۡضِ مَآ أَنتَ قَاضٍۖ
إِنَّمَا تَقۡضِي هَٰذِهِ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَآ ﴿٧٢﴾ إِنَّآ ءَامَنَّا بِرَبِّنَا لِيَغۡفِرَ لَنَا خَطَٰيَٰنَا وَمَآ أَكۡرَهۡتَنَا
عَلَيۡهِ مِنَ ٱلسِّحۡرِۗ وَٱللَّهُ خَيۡرٞ وَأَبۡقَىٰٓ ﴿٧٣﴾

**72-73.** ከመጡልን ተዐምራቶችና ከዚያ ከፈጠረን አምላክ ፈጽሞ አናስበልጥህም። እናም አንተም የምትፈርደውን ፍረድ። የምትፈርደው በዚህች በአነስተኛይቱ ህይወት ብቻ ላይ ነውና አሉት። ኃጢአቶቻችንንና ከድግምትም እንድንፈፅመው ያስገደድከንን ይምረን ዘንድ እኛ በጌታችን አምነናል። አላህ በጣም በላጭ ነው። ቅጣቱም ሆነ ምንዳው በጣም የሚዘወትር ነው አሉ።

إِنَّهُۥ مَن يَأۡتِ رَبَّهُۥ مُجۡرِمٗا فَإِنَّ لَهُۥ جَهَنَّمَ لَا يَمُوتُ فِيهَا وَلَا يَحۡيَىٰ ﴿٧٤﴾ وَمَن يَأۡتِهِۦ مُؤۡمِنٗا
قَدۡ عَمِلَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَأُوْلَٰٓئِكَ لَهُمُ ٱلدَّرَجَٰتُ ٱلۡعُلَىٰ ﴿٧٥﴾ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا
ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ وَذَٰلِكَ جَزَآءُ مَن تَزَكَّىٰ ﴿٧٦﴾

**74-76.** እነሆ ከሃዲ ሆኖ ወደ ጌታው የሚመጣ (የሚሞት) ሰው ለእርሱ ገሀነም አለችለት። በውስጧም አይሞትም ህያውም አይሆንም። እነዚያ በጎ ስራዎችን የሰሩና አማኝ ሆነው ወደ ጌታቸው የመጡ ሰዎች ደግሞ ለእነርሱ ከፍተኛ ደረጃዎች አሏቸው። ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው የመኖሪያ ገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲሆኑ አሏቸው። ይህ አይነቱ ክፍያ የተጥራራ ሰው ሁሉ ምንዳ ነው።

وَلَقَدْ أَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنْ أَسْرِ بِعِبَادِى فَٱضْرِبْ لَهُمْ طَرِيقًا فِى ٱلْبَحْرِ يَبَسًا لَّا تَخَٰفُ دَرَكًا وَلَا تَخْشَىٰ ﴿٧٧﴾ فَأَتْبَعَهُمْ فِرْعَوْنُ بِجُنُودِهِۦ فَغَشِيَهُم مِّنَ ٱلْيَمِّ مَا غَشِيَهُمْ ﴿٧٨﴾ وَأَضَلَّ فِرْعَوْنُ قَوْمَهُۥ وَمَا هَدَىٰ ﴿٧٩﴾

**77-79.** ወደ ሙሳ ባሮቼን ይዘህ በሌሊት ሂድ። ለእነርሱም በባህር ውስጥ ደረቅ መንገድን አድርግላቸው። ፈርዖን ያገኘኛል ብለህ አትፍራ። ከመስመጥም አትጨነቅ ስንል በእርግጥ ላክንበት። ፈርዖን ከሰራዊቱ ጋር ሆኖ ተከተላቸው። ከባህሩም የሚሸፍን ነገር ሸፈናቸው። ፈርዖን ህዝቦቹን አሳሳታቸው። ቅኑንም መንገድ አልመራቸውም።

يَٰبَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ قَدْ أَنجَيْنَٰكُم مِّنْ عَدُوِّكُمْ وَوَٰعَدْنَٰكُمْ جَانِبَ ٱلطُّورِ ٱلْأَيْمَنَ وَنَزَّلْنَا عَلَيْكُمُ ٱلْمَنَّ وَٱلسَّلْوَىٰ ﴿٨٠﴾ كُلُوا۟ مِن طَيِّبَٰتِ مَا رَزَقْنَٰكُمْ وَلَا تَطْغَوْا۟ فِيهِ فَيَحِلَّ عَلَيْكُمْ غَضَبِى ۖ وَمَن يَحْلِلْ عَلَيْهِ غَضَبِى فَقَدْ هَوَىٰ ﴿٨١﴾ وَإِنِّى لَغَفَّارٌ لِّمَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا ثُمَّ ٱهْتَدَىٰ ﴿٨٢﴾

**80-82.** የኢስራኤል ልጆች ሆይ ከጠላታችሁ በእርግጥ አዳንናችሁ። በጡር ተራራም ቀኝ ጎን ቀጠሮ አደረግንላችሁ። በእናንተም ላይ መንንና ሰልዋን (ድርጭትን) አወረድንላችሁ። ከሰጠናችሁ ሲሳይ ከመልካሙ ብሉ በእርሱም ወሰንን አትለፉ። ቁጣዬ በእናንተ ላይ ይወርድባችኋልና። በእርሱም ላይ ቁጣዬ የሚወርድበት ሰው ሁሉ በእርግጥ ይጠፋል። እኔም ለተፀፀተ ላመነም መልካምንም ለሰራ ከዚያ ለተመራ ሰው በእርግጥ መሓሪ ነኝ።

۞ وَمَآ أَعْجَلَكَ عَن قَوْمِكَ يَٰمُوسَىٰ ﴿٨٣﴾ قَالَ هُمْ أُو۟لَآءِ عَلَىٰٓ أَثَرِى وَعَجِلْتُ إِلَيْكَ رَبِّ لِتَرْضَىٰ ﴿٨٤﴾ قَالَ فَإِنَّا قَدْ فَتَنَّا قَوْمَكَ مِنۢ بَعْدِكَ وَأَضَلَّهُمُ ٱلسَّامِرِىُّ ﴿٨٥﴾

83-85. ሙሳ ሆይ! ከህዝቦችህ ምን አስቸኮለህም ተባለ። እነርሱ እነዚህ በዱካዬ ላይ ያሉ ናቸው። ጌታዬ ሆይ! ትወድልኝ ዘንድ ወደ አንተ ቸኮልኩ አለ። (አላህ) እኛም ከአንተ በኋላ ሰዎችህን በእርግጥ ፈተን። ሳምራዊውም* አሳሳታቸው አለው።

* ይህ ሰው ከብቶችን ከሚገዙ እንስሳ አምላኪዎች አንዱ ነበር። ሙሳ በሄዱበት አጋጣሚ ጌጣጌጦችን በመሰብሰብ ወይፍን አስመስሎ በመስራትና ሰዎችን ወደዚህ እሱን እንዲያመልኩ በመገፋፋት ህዝቦችን እምነት አበላሽቶ ቆያቸው።

فَرَجَعَ مُوسَىٰٓ إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ غَضۡبَٰنَ أَسِفٗاۚ قَالَ يَٰقَوۡمِ أَلَمۡ يَعِدۡكُمۡ رَبُّكُمۡ وَعۡدًا حَسَنًاۚ أَفَطَالَ عَلَيۡكُمُ ٱلۡعَهۡدُ أَمۡ أَرَدتُّمۡ أَن يَحِلَّ عَلَيۡكُمۡ غَضَبٞ مِّن رَّبِّكُمۡ فَأَخۡلَفۡتُم مَّوۡعِدِي ٨٦

86. ሙሳም ወደ ሰዎች የተቆጣና ያዘነ ሆኖ ተመለሰ። ህዝቦቼ ሆይ! ጌታችሁ መልካም ተስፋን አልቀጠራችሁምን? ቀጠሮው በእናንተ ላይ ረዘመባችሁን? ወይስ በእናንተ ላይ ከጌታችሁ ቅጣት ሊወርድባችሁ ፈለጋችሁና ቃል ኪዳኔን አፈረሳችሁን? አላቸው።

قَالُواْ مَآ أَخۡلَفۡنَا مَوۡعِدَكَ بِمَلۡكِنَا وَلَٰكِنَّا حُمِّلۡنَآ أَوۡزَارٗا مِّن زِينَةِ ٱلۡقَوۡمِ فَقَذَفۡنَٰهَا فَكَذَٰلِكَ أَلۡقَى ٱلسَّامِرِيُّ ٨٧

87. ቀጠሮህን በፈቃዳችን አልጣስንም። ግን እኛ ከህዝቦቹ ጌጥ ሸክሞችን ተጫንን። በእሳት ላይ ጣልናትም። ሳምራዊውም እንደዚሁ አብሮን ጣለ አሉት።

فَأَخۡرَجَ لَهُمۡ عِجۡلٗا جَسَدٗا لَّهُۥ خُوَارٞ فَقَالُواْ هَٰذَآ إِلَٰهُكُمۡ وَإِلَٰهُ مُوسَىٰ فَنَسِيَ ٨٨ أَفَلَا يَرَوۡنَ أَلَّا يَرۡجِعُ إِلَيۡهِمۡ قَوۡلٗا وَلَا يَمۡلِكُ لَهُمۡ ضَرّٗا وَلَا نَفۡعٗا ٨٩

88-89. ለእሱም አካል የሆነና ለእርሱ የመጓጎር ባህሪ ያለውን ጥጃን አወጣላቸው። ተከታዮች ሆይ፣ ይህ የእናንተም ሆነ የሙሳ አምላክ ነው። ግን ረሳው እንጂ አሉ። ወደ እነርሱ ንግግርን የማይመልስ ለእነርሱም ጉዳትንና ጥቅምን የማይችል መሆኑን አያዩምን?

وَلَقَدۡ قَالَ لَهُمۡ هَٰرُونُ مِن قَبۡلُ يَٰقَوۡمِ إِنَّمَا فُتِنتُم بِهِۦۖ وَإِنَّ رَبَّكُمُ ٱلرَّحۡمَٰنُ فَٱتَّبِعُونِي وَأَطِيعُوٓاْ أَمۡرِي ٩٠ قَالُواْ لَن نَّبۡرَحَ عَلَيۡهِ عَٰكِفِينَ حَتَّىٰ يَرۡجِعَ إِلَيۡنَا مُوسَىٰ ٩١

**90-91.** ከዚያ በፊት ሀሩንም በእርግጥ አላቸው፡፡ ህዝቦቼ ሆይ፣ ይህ በእርሱ የተሞከራችሁበት ብቻ ነው፡፡ ጌታችሁም አልረህማን ነው፡፡ ተከተሉኝም፤ ትእዛዜንም ስሙ፡፡ ሙሳ ወደ እኛ እስከሚመለስ በእርሱ መገዛት ላይ ከመቆየት ፈጽሞ አንወገድም አሉ፡፡

قَالَ يَٰهَٰرُونُ مَا مَنَعَكَ إِذْ رَأَيْتَهُمْ ضَلُّوٓاْ ﴿٩٢﴾ أَلَّا تَتَّبِعَنِۖ أَفَعَصَيْتَ أَمْرِي ﴿٩٣﴾
قَالَ يَبْنَؤُمَّ لَا تَأْخُذْ بِلِحْيَتِي وَلَا بِرَأْسِيٓۖ إِنِّي خَشِيتُ أَن تَقُولَ فَرَّقْتَ بَيْنَ بَنِيٓ إِسْرَٰٓءِيلَ
وَلَمْ تَرْقُبْ قَوْلِي ﴿٩٤﴾

**92-94.** ሙሳ፡- ሃሩን ሆይ! ተሳስተው ባየሃቸው ጊዜ እኔን ከመከተል ምን ከለከህ? ትእዛዜን ጣስክን? አለ፡፡ ሃሩን የእናቴ ልጅ ሆይ! ፂሜንም ሆነ ራሴን አትያዝ፡፡ እኔ በኢስራኤል ልጆች መካከል ለያየህ ቃሌንም አልጠበክም ማለትህን ፈራሁና አለው፡፡

قَالَ فَمَا خَطْبُكَ يَٰسَٰمِرِيُّ ﴿٩٥﴾ قَالَ بَصُرْتُ بِمَا لَمْ يَبْصُرُواْ بِهِۦ فَقَبَضْتُ قَبْضَةً مِّنْ أَثَرِ
ٱلرَّسُولِ فَنَبَذْتُهَا وَكَذَٰلِكَ سَوَّلَتْ لِي نَفْسِي ﴿٩٦﴾

**95-96.** ሙሳ ሳምራዊው ሆይ! ነገርህ ምንድን ነው? አለ፡፡ ሳምራዊው እነርሱ ያላዩትን ነገር አየሁ፡፡ ከመልዕክተኛው ፈረስ ኮቴ ዱካም ጭብጥ ዐፈርን ዘገንኩ፡፡ በቅርፁ ላይ ጣልኳትም፡፡ እንደዚሁም ነፍሴ ሸለመችልኝ አለ፡፡

قَالَ فَٱذْهَبْ فَإِنَّ لَكَ فِي ٱلْحَيَوٰةِ أَن تَقُولَ لَا مِسَاسَۖ وَإِنَّ لَكَ مَوْعِدًا لَّن تُخْلَفَهُۥۖ وَٱنظُرْ
إِلَىٰٓ إِلَٰهِكَ ٱلَّذِي ظَلْتَ عَلَيْهِ عَاكِفًاۖ لَّنُحَرِّقَنَّهُۥ ثُمَّ لَنَنسِفَنَّهُۥ فِي ٱلْيَمِّ نَسْفًا ﴿٩٧﴾

**97.** ሙሳ ለሳምራዊው ሂድ አለው፡፡ በህይወትህ ለአየኸው ሰው ሁሉ መነካካት የለም እያልክ ኑር፡፡ ለአንተም ፈጽሞ የማትቀር ቀጠሮም አለህ፡፡ ወደ እዚያም በእርሱ ላይ ተገዢው ሆነህ ወደ ቆየህበት አምላክህ ተመልከት፡፡ በእርግጥ እናቃጥለዋለን፡፡ ከዚያ በባህሩ ውስጥ እንበትነዋለን፡፡

إِنَّمَآ إِلَٰهُكُمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ وَسِعَ كُلَّ شَيْءٍ عِلْمًا ﴿٩٨﴾

**98.** (ሰዎች ሆይ!) ጌታችሁ ያ ከእርሱ በስተቀር ሌላ አምላክ የሌለ የሆነው አላህ ብቻ ነው፡፡ እውቀቱ ሁሉን ነገር አዳረሰ፡፡

**ከጧሃ ከአንቀፅ (72-98) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. በእውነት ላይ ውሸት በእምነት ላይ ደግሞ ክህደት ተፅዕኖ ሊያሳድር እንደማይችል፤
2. የዱንያ ቅጣት ያሻውን ያህል ቢከብድ ከአኼራ ቅጣት ጋር ሊወዳደር እንደማይችል፤
3. በላይ እስካልሆነ ድረስ ክህደትን ማስወገድ እንደማይፈቅድ
4. የነብዩን ነቢይነት ማረጋገጥ፤
5. አላህ በባህር ውስጥ ደረቅ መንገድ አስገኝቶ የሙሳ ሰዎች በሰላም እንዲያልፉ ማድረጉ፦
6. በነብዩ (ﷺ) ጊዜ የነበሩ አይሁዶችን ለአያቶቻቸው የዋለውን ውለታ በማስታወስ ኢስላምን እንዲቀበሉ ግፊት ማሳደር፤
7. ማባከንና ግፍ መስራት እንዲሁም የአላህን ፀጋ መካድ ክልክል ስለመሆኑ፤
8. መቆጣት ከአላህ ባህሪዎች አንዱ ስለመሆኑ፤
9. ችኮላን ማውገዝና ሙስሊሞችንም ከመቸኮል ማስጠንቀቅ፤
10. የአላህን ውዴታ መለመን ተገቢ ስለመሆኑ፤
11. ለአላህ ብሎ መቆጣትም ሆነ ማዘን ተገቢና የነብያት ተግባር ስለ መሆኑ፤
12. ሴቶች እርስ በራሳቸው ጌጣጌጦችን መዋዋስ ተገቢ ስለመሆኑ፤
13. አዕምሮ እውነትንና ውሸትን፤ መጥፎና ደግን ለመለየት የሚያስችል ትልቅ መሳሪያ ስለ መሆኑ፤
14. ነብይን አለመታዘዝ ለከፍተኛ ፈትና እንደሚያበቃ፤
15. ወዳጅ ወይም ዘመድ እንኳን ቢሆን ባጠፋ ጊዜ መውቀስ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
16. ተወቃሽ ስህተት ካለው ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት፤
17. ነብያትም ቢሆኑ ሀቅን ለማግኘት በሚያደርጉት ጥረት ሊሳሳቱ እንደሚችሉ፤
18. የተጠራጠረን ሰው እንዲናገር ማድረጉ ተገቢ ስለመሆኑ፤
19. የተሳሳተን ሰው ማውገዝም ሆነ ማኩረፍ እንዲሁም ማግለል ተገቢ ስለመሆኑ፤
20. በዓድ አምልኮትን ከህዝብ የአኗኗር የእምነት ስርዓት ማስወገድ፤ ስዕሉን ወይም ጣኦቱን መሰባበር አቅሙ ላለው ሰው ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

كَذَٰلِكَ نَقُصُّ عَلَيْكَ مِنْ أَنۢبَآءِ مَا قَدْ سَبَقَ ۚ وَقَدْ ءَاتَيْنَٰكَ مِن لَّدُنَّا ذِكْرًا ﴿٩٩﴾ مَّنْ أَعْرَضَ
عَنْهُ فَإِنَّهُۥ يَحْمِلُ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ وِزْرًا ﴿١٠٠﴾ خَٰلِدِينَ فِيهِ ۖ وَسَآءَ لَهُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ حِمْلًا ﴿١٠١﴾

**99-101.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እንደዚሁ በእርግጥ ካለፉት ወሬዎች በአንተ ላይ እንተርካለን ከእኛም ዘንድ ቁርኣንን በእርግጥ ሰጠንህ። ከእርሱ ያፈገፈገ ሰው እርሱ በትንሳኤ ቀን ከባድን ቅጣት ይሸከማል። በእርሱ ውስጥ ዘውታሪዎች ሆነው ይሸከማሉ። በትንሳኤ ቀን ለእነርሱ እጣ ፈንታ የሆነው ሸክም ከፋ!

يَوْمَ يُنفَخُ فِى ٱلصُّورِ ۚ وَنَحْشُرُ ٱلْمُجْرِمِينَ يَوْمَئِذٍ زُرْقًا ﴿١٠٢﴾ يَتَخَٰفَتُونَ بَيْنَهُمْ إِن لَّبِثْتُمْ
إِلَّا عَشْرًا ﴿١٠٣﴾ نَّحْنُ أَعْلَمُ بِمَا يَقُولُونَ إِذْ يَقُولُ أَمْثَلُهُمْ طَرِيقَةً إِن لَّبِثْتُمْ إِلَّا يَوْمًا ﴿١٠٤﴾

**102-104.** በቀንዱ በሚነፋ ቀን ሽከማቸው ከፋ። ከሓዲያን በዚያ ቀን ዓይኖቻቸው ሰማያዊዎች ሆነው እንሰበስባቸዋለን። ዐስርን ቀን እንጂ አልቆያችሁም በመባባል በመካከላቸው ይሾካሾካሉ። በሃሳብ ቀጥተኛቸው አንድን ቀን እንጂ አልቆያችሁም በሚል ጊዜ የሚሉትን ነገር እኛ ዐዋቂዎች ነን።

وَيَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلْجِبَالِ فَقُلْ يَنسِفُهَا رَبِّى نَسْفًا ﴿١٠٥﴾ فَيَذَرُهَا قَاعًا صَفْصَفًا ﴿١٠٦﴾
لَّا تَرَىٰ فِيهَا عِوَجًا وَلَآ أَمْتًا ﴿١٠٧﴾

**105-107.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጋራዎች ይጠይቁሃልና ጌታዬ መበተንን ይበትናቸዋል በላቸው። ትክክል ሜዳም ሆና ይተዋታል። በእርሷ ዝቅታና ከፍታን ፈፅሞ አታይም።

يَوْمَئِذٍ يَتَّبِعُونَ ٱلدَّاعِىَ لَا عِوَجَ لَهُۥ ۖ وَخَشَعَتِ ٱلْأَصْوَاتُ لِلرَّحْمَٰنِ فَلَا تَسْمَعُ إِلَّا هَمْسًا ﴿١٠٨﴾ يَوْمَئِذٍ
لَّا تَنفَعُ ٱلشَّفَٰعَةُ إِلَّا مَنْ أَذِنَ لَهُ ٱلرَّحْمَٰنُ وَرَضِىَ لَهُۥ قَوْلًا ﴿١٠٩﴾ يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ
وَلَا يُحِيطُونَ بِهِۦ عِلْمًا ﴿١١٠﴾ ۞ وَعَنَتِ ٱلْوُجُوهُ لِلْحَىِّ ٱلْقَيُّومِ ۖ وَقَدْ خَابَ مَنْ حَمَلَ ظُلْمًا ﴿١١١﴾

**108-111.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዚያ ቀን ለመሰብሰብ ጠሪውን ምንም እንከን የሌለውን ተጣሪ ይከተላሉ። ድምፆች ሁሉ ለአልረህማን ፀጥ ይላሉ። ስለዚህ ሹክሹክታን እንጂ አትሰማም። በዚያ ቀን ለእርሱ አልረህማን የፈቀደለትንና ለእርሱም ቃልን የወደደለትን ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ ምልጃ አንድንም ሰው አትጠቅምም። በስተፊታቸው ያለውንም ሆነ በስተኋላቸው ያለውን ሁሉ ያውቃል። በእርሱ ላይ ግን ማንም ሰው በእውቀት አያካብበም። ፊቶችም ሁሉ ህያውና የሁሉ አስተናባሪ ለሆነው አላህ ተዋረዱ። በደልንም የተሸከመ ሰው በእርግጥ ከሰረ።

وَمَن يَعْمَلْ مِنَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَهُوَ مُؤْمِنٌ فَلَا يَخَافُ ظُلْمًا وَلَا هَضْمًا ﴿١١٢﴾ وَكَذَٰلِكَ أَنزَلْنَٰهُ
قُرْءَانًا عَرَبِيًّا وَصَرَّفْنَا فِيهِ مِنَ ٱلْوَعِيدِ لَعَلَّهُمْ يَتَّقُونَ أَوْ يُحْدِثُ لَهُمْ ذِكْرًا ﴿١١٣﴾

**112-113.** እርሱ አማኝ ሆኖ መልካም ስራዎችን የሰራ ሰው በደልንም ሆነ መጉደልን አይፈራም። እንደዚሁም ዐረብኛ ቁርኣን ሆኖ አወረድነው። አላህን ይፈሩ ዘንድ ወይም ለእነርሱ ግሣጼን ያድስላቸው ዘንድ ከዛቻ ደጋግመን በውስጡ ገለጽን።

**ከጧሃ ምዕራፍ ከአንቀፅ (99-112) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
2. ቁርኣን ለአስተዋዮች መመሪያ እንደሚሆን፤
3. በቁርኣን የማይሰሩ አመፀኞች የቂያማ ቀን ባህሪያቸው እንደሚከፋ፤
4. ከቂያማ ቀን ጭንቅ ክብደት የተነሳ የሰው ልጅ በእልፍ አእላፍ የሚቆጠሩ የዱንያ አመቶችን አንድ ቀን እንጂ ከዚያ በላይ እንዳሳለፈ እንደሚቆጠር፤
5. አጋሪዎች ምን ያህል ደንቆሮ እንደሆኑ በግልፅ ማሳየት፤
6. የሙቶ መነሳትን ሐቅኝነት ማረጋገጥ፤
7. ከአላህ ዘንድ ሽምግልና ለተውሒድ ሰዎች እንጂ ለሙሽሪክ ወይም ለአጋሪዎች ሽፈአ ሊሆን እንደማይችልና ለእነሱም ማንም እንደማይሸመግል ማረጋገጥን እንማራለን።

فَتَعَٰلَى ٱللَّهُ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡحَقُّۗ وَلَا تَعۡجَلۡ بِٱلۡقُرۡءَانِ مِن قَبۡلِ أَن يُقۡضَىٰٓ إِلَيۡكَ وَحۡيُهُۥۖ
وَقُل رَّبِّ زِدۡنِي عِلۡمٗا ١١٤

**114.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እውነተኛው ንጉስ አላህ ከሓዲያን ከሚሉት ነገር ሁሉ ላቀ። ወደ አንተ መወረዱም ከመፈፀሙ በፊት በማንበብ አትቸኩል። ጌታዬ ሆይ፣ ዕውቀትን ጨምርልኝ በል።

ከጧሃ ምዕራፍ (114) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ ጅብሪል በመጣላቸው ጊዜ ያስተማራቸው እንዳይረሳቸው በጣም ይሰጉና አብረውት ይጣደፉ ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَلَقَدۡ عَهِدۡنَآ إِلَىٰٓ ءَادَمَ مِن قَبۡلُ فَنَسِيَ وَلَمۡ نَجِدۡ لَهُۥ عَزۡمٗا ١١٥ وَإِذۡ قُلۡنَا لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ
ٱسۡجُدُواْ لِأٓدَمَ فَسَجَدُوٓاْ إِلَّآ إِبۡلِيسَ أَبَىٰ ١١٦ فَقُلۡنَا يَٰٓـَٔادَمُ إِنَّ هَٰذَا عَدُوّٞ لَّكَ وَلِزَوۡجِكَ فَلَا
يُخۡرِجَنَّكُمَا مِنَ ٱلۡجَنَّةِ فَتَشۡقَىٰٓ ١١٧ إِنَّ لَكَ أَلَّا تَجُوعَ فِيهَا وَلَا تَعۡرَىٰ ١١٨ وَأَنَّكَ لَا تَظۡمَؤُاْ
فِيهَا وَلَا تَضۡحَىٰ ١١٩ فَوَسۡوَسَ إِلَيۡهِ ٱلشَّيۡطَٰنُ قَالَ يَٰٓـَٔادَمُ هَلۡ أَدُلُّكَ عَلَىٰ شَجَرَةِ ٱلۡخُلۡدِ
وَمُلۡكٖ لَّا يَبۡلَىٰ ١٢٠ فَأَكَلَا مِنۡهَا فَبَدَتۡ لَهُمَا سَوۡءَٰتُهُمَا وَطَفِقَا يَخۡصِفَانِ عَلَيۡهِمَا مِن
وَرَقِ ٱلۡجَنَّةِۚ وَعَصَىٰٓ ءَادَمُ رَبَّهُۥ فَغَوَىٰ ١٢١

**115-121.** ወደ አደም ከዚህ በፊት ቃል ኪዳንን በእርግጥ አወረድንና ረሳ። ለእርሱም ቆራጥነትን አላገኘንለትም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለመላእክት ለአደም ስገዱ ባልን ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ኢብሊስ ብቻ ሲቀር ሰገዱ። እሱማ እምቢ አለ። ከዚያ አልን። አደም ሆይ! ይህ ለአንተም ለሚስትህም በእርግጥ ጠላት ነው። ስለዚህ ከገነት አያውጣችሁ፤ ትለፋለህና።

አደም ሆይ፣ ለአንተ በእርሷ ውስጥ አለመራብና አለመታረዝ አለህ። አንተም ከእርሷ ውስጥ አትጠማም። በፀሐይም አትተኮስም። ሰይጣን ወደ እርሱ እንዲህ ሲል አደም ሆይ፣ በመዘውተሪያ ዛፍ በማይጠፋ ንግስናም ላይ ላመላክትህን በማለት እርሱን ጎተጎተ። ከእርሷም በሉ። ለእነርሱም ሀፍረተ ገላቸው ተገለፀች። ከገነትም ቅጠል በላያቸው ላይ ይለጥፉ ጀመር። አደምም የጌታውን ትእዛዝ ረስቶ ጣሰ። (ከፈለገው መዘውተር) ተሳሳተም።

ثُمَّ ٱجْتَبَٰهُ رَبُّهُۥ فَتَابَ عَلَيْهِ وَهَدَىٰ ﴿١٢٢﴾ قَالَ ٱهْبِطَا مِنْهَا جَمِيعًۢا ۖ بَعْضُكُمْ لِبَعْضٍ عَدُوٌّ ۖ
فَإِمَّا يَأْتِيَنَّكُم مِّنِّى هُدًى فَمَنِ ٱتَّبَعَ هُدَاىَ فَلَا يَضِلُّ وَلَا يَشْقَىٰ ﴿١٢٣﴾

**122-123.** ከዚያም ጌታው መረጠው ከእርሱም ፀፀቱን ተቀበለው መራውም። አላህ አላቸው፡- ከፊላችሁ ለከፊሉ ጠላት ሲሆን አደምና ሐዋ ሁላችሁም ከእርሷ ውረዱ። ከእኔ የሆነ መሪ (መመሪያ) ቢመጣላችሁ መሪዬን የተከተለ አይሳሳትም። አይቸገርምም።

وَمَنْ أَعْرَضَ عَن ذِكْرِى فَإِنَّ لَهُۥ مَعِيشَةً ضَنكًا وَنَحْشُرُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ أَعْمَىٰ ﴿١٢٤﴾ قَالَ رَبِّ
لِمَ حَشَرْتَنِىٓ أَعْمَىٰ وَقَدْ كُنتُ بَصِيرًا ﴿١٢٥﴾ قَالَ كَذَٰلِكَ أَتَتْكَ ءَايَٰتُنَا فَنَسِيتَهَا ۖ وَكَذَٰلِكَ ٱلْيَوْمَ
تُنسَىٰ ﴿١٢٦﴾ وَكَذَٰلِكَ نَجْزِى مَنْ أَسْرَفَ وَلَمْ يُؤْمِنۢ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِۦ ۚ وَلَعَذَابُ ٱلْءَاخِرَةِ أَشَدُّ وَأَبْقَىٰٓ ﴿١٢٧﴾

**124-127.** ከግሳጼዬ የዞረ ሰው ግን በዚህች ዐለም ጠባብ ኑሮ አለው። በትንሳኤ ቀንም ዕውር ሆኖ እንቀሰቅሰዋለን። ጌታዬ ሆይ! ለምን ዕውር አድርገህ አስነሳኸኝ። በእርግጥ የማይ የነበርኩ ስሆን ይላል። ነገሩ እንደዚሁ ነው። ተዐምራታችን መጣችልህ ተውካትም። እንደዚሁም ዛሬ ትተዋለህ ይለዋል። እንደዚሁም ያጋራንና በጌታው አንቀፆች ያላመነን ሰው እንቀጣዋለን። የመጨረሻይቱ ዓለም ቅጣት በጣም ብርቱና ለሁልጊዜም ዘውታሪ ነው።

أَفَلَمْ يَهْدِ لَهُمْ كَمْ أَهْلَكْنَا قَبْلَهُم مِّنَ ٱلْقُرُونِ يَمْشُونَ فِى مَسَٰكِنِهِمْ ۗ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ
لِّأُو۟لِى ٱلنُّهَىٰ ﴿١٢٨﴾ وَلَوْلَا كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ لَكَانَ لِزَامًا وَأَجَلٌ مُّسَمًّى ﴿١٢٩﴾

**128-129.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቁረይሾች ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች ብዙዎችን ያጠፋን መሆናችን በመኖሪያዎቻቸው የሚሄዱ ሆነው ሳሉ ለእነርሱ አልተገለፀላቸውምን? በዚህ ውስጥ ለአእምሮ ባለ ቤቶች በእርግጥ መልዕክቶች አሉበት። ከጌታህ ያለፈች ቃልና የተወሰነ ጊዜ ባልነበረ ኖሮ ቅጣቱ አሁኑ የሚይዛቸው ይሆን ነበር።

فَٱصۡبِرۡ عَلَىٰ مَا يَقُولُونَ وَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ قَبۡلَ طُلُوعِ ٱلشَّمۡسِ وَقَبۡلَ غُرُوبِهَاۖ وَمِنۡ ءَانَآيِٕ ٱلَّيۡلِ فَسَبِّحۡ وَأَطۡرَافَ ٱلنَّهَارِ لَعَلَّكَ تَرۡضَىٰ ﴿١٣٠﴾ وَلَا تَمُدَّنَّ عَيۡنَيۡكَ إِلَىٰ مَا مَتَّعۡنَا بِهِۦٓ أَزۡوَٰجٗا مِّنۡهُمۡ زَهۡرَةَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا لِنَفۡتِنَهُمۡ فِيهِۚ وَرِزۡقُ رَبِّكَ خَيۡرٞ وَأَبۡقَىٰ ﴿١٣١﴾ وَأۡمُرۡ أَهۡلَكَ بِٱلصَّلَوٰةِ وَٱصۡطَبِرۡ عَلَيۡهَاۖ لَا نَسۡـَٔلُكَ رِزۡقٗاۖ نَّحۡنُ نَرۡزُقُكَۗ وَٱلۡعَٰقِبَةُ لِلتَّقۡوَىٰ ﴿١٣٢﴾

**130-132.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሚሉት ሁሉ ላይ ታገሥ፤ ጌታህን ፀሐይ ከመውጣትዋ በፊትና ከመግባቷም በፊት የምታመሰግን ሆነህ አጥራው። ከሌሊት ሰዓቶችም በቀን ጫፎችም አጥራው። በሚሰጥህ ምንዳ ልትወድ ይከጀላልና። ዐይኖችህን ከሰዎች የተወሰኑ ክፍሎችን በርሱ ልንፈትናቸው ወደ አጣቀምንበት ወደ ቅርቢቱ ህይወት ጌጦች አትዘርጋ። የጌታህ ሲሳይ በጣም በላጭና ዘውታሪ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቤተሰብህን በሶላት ላይ እዘዝ። አንተም በእርሷ ላይ ዘውትር። ሲሳይን አንጠይቅህም። እኛ እንሰጥሃለን። መልካሚቱ መጨረሻ ለጥንቁቆች ሁሉ ናት።

وَقَالُواْ لَوۡلَا يَأۡتِينَا بِـَٔايَةٖ مِّن رَّبِّهِۦٓۚ أَوَلَمۡ تَأۡتِهِم بَيِّنَةُ مَا فِي ٱلصُّحُفِ ٱلۡأُولَىٰ ﴿١٣٣﴾ وَلَوۡ أَنَّآ أَهۡلَكۡنَٰهُم بِعَذَابٖ مِّن قَبۡلِهِۦ لَقَالُواْ رَبَّنَا لَوۡلَآ أَرۡسَلۡتَ إِلَيۡنَا رَسُولٗا فَنَتَّبِعَ ءَايَٰتِكَ مِن قَبۡلِ أَن نَّذِلَّ وَنَخۡزَىٰ ﴿١٣٤﴾

**133-134.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተከራካሪዎችህ ከጌታው በሆነ ተዐምር አይመጣምን? አሉ። በመጀመሪያዎቹ ፁሁፎች ውስጥ ያለችው ማስረጃ አልመጣቻቸውምን? እኛም ከሙሐመድ መላክ በፊት በቅጣት ባጠፋናቸው ኖሮ ጌታችን ሆይ! ከመዋረዳችንና✴ ከማፈራችን በፊት አንቀፆችህን እንከተል ዘንድ ወደኛ መልዕክተኛን አትልክልንም ነበርን? ባሉ ነበር።

✴ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብሏል፡- «ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጧሊብ ንፁህ ያልተነጠረ ትንሽ ወርቅ በቆዳ አሽገው ወደ አላህ መልዕክተኛ ላኩ። እሳቸውም ለአራት ሰዎች ማለትም ለውየይ ኢብኑ በድር፤ ለዐቅርዕ ኢብኑ ሓቢስ፤ ለዘይድ አልኸይል አራተኛው ደግሞ ለዐርቀማህ ወይም ለዓሚር ኢብኑ አጥጡፈይል አከፋፈሏቸው። ከሱሓባዎች መካከል አንዱ «እኛ ከነርሱ ይበልጥ በዚህ የተገባን ነበርን» አለ። ይህም ወሬ ነብዩ ዘንድ ደረሰ። እሳቸውም «እኔ ታማኝ ሆኜ ቀንና ሌሊት ከሰማይ መለኮታዊ መልዕክት እየመጣልኝ እናንተ አታምኑኝምን?» አሉ። አንድ ዓይኖቹ ወደ ውስጥ የጎደጎዱ ጉንጮቹ ያሰረጎዱ ግንባሩ የተሸበሸበ፤ ጢሙ ችምችም ያለ፤ ፀጉሩ የተላጨና ቀበቶ የታጠቀ ሰው ተነስቶ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህን ፍራ!» አላቸው። እሳቸውም «ወየውልህ! በምድር ላይ ካሉ ሰዎች በላይ አላህን በመፍራት በኩል የተገባሁ አይደለሁምን?» አሉ። ሰውየውም ሄደ። ይህ ጊዜ ኻሊድ ኢብኑ ወሊድ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አንገቱን ልቁረጠውን»

አላቸው። እሳቸውም «በፍፁም! ምናልባት የሚሰግድ ይሆናል» አሉት። እሱም «ከሰጋጆች መካከል ስንቱ ነው በልቦናው የሌለውን በምላሱ የሚናገረው» አላቸው። እሳቸውም «እኔ የሰው ልጆችን ልቦና እንድመረምር ወይም ሆዳቸውን እንድቀድ አልታዘዝኩም» አሉት። ከዚያም ሰውየው እያዘገመ ሲሄድ ተመለከቱና «ከዚህ ሰው የሚወጡና ቁርኣንን በየቀኑና በተከታታይ የሚያነቡ፤ ነገር ግን አነባበባቸው ከጉሮሯቸው በታች የማይዘልቅ ልክ ቀስት ከደጋኑ ተስፈንጥሮ እንደሚወጣ ሁሉ እነርሱም ከሃይማኖታቸው ተስፈንጥረው የሚወጡ የሆኑ ትውልዶች ይፈጠራሉ» አሉ። አቡ ሰዒድ አልኹድሪይ ነብዩ (ﷺ) «ባገኛቸው ኖሮ የሰሙድ ሕዝቦች በተገደሉበት አኳኋን በእርግጥ እገድላቸው ነበር» አሉ ብለዋል።

قُلۡ كُلّٞ مُّتَرَبِّصٞ فَتَرَبَّصُواْۖ فَسَتَعۡلَمُونَ مَنۡ أَصۡحَٰبُ ٱلصِّرَٰطِ ٱلسَّوِيِّ وَمَنِ ٱهۡتَدَىٰ ١٣٥

**135.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁሉም ተጠባባቂ ነው ተጠባበቁም የቀጥታውም መንገድ ባለቤቶች እነማን እንደ ሆኑ እነማንም እንደ ተመሩ ወደ ፊት ታውቃላችሁ በላቸው።

**ከጧሃ ምዕራፍ ከአንቀፅ (113-135) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎች፡-**

1. ቁርኣን በአረብኛ የመውረዱ ምክንያት ምን እንደሆነ መጠቆም፤
2. የአላህ ኃያልነትና ከልጅም ሆነ ከአጋር የፀዳ መሆኑ፤
3. ቁርኣንን በጥሞና ማንበብም ሆነ በቀስታ መረዳት ለያንዳንዳችን ተገቢ ስለ መሆኑ፤
4. እውቀትን ለመጨመር ግፊት ማሳደር፤
5. አባታችን አደም ረስተው እንደነበረ በማስታወስ መፅናናት እንዳለኢብኑ
6. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
7. ኢብሊስ ለአደም ልጆች ሁሉ ያለውን ጠላትነት ማረጋገጥ፤
8. ልፋት በምድር እንጂ በጀነት እንደሌለ፤
9. የኢብሊስን ጉጉት መቀበልና ማስተናገድ ሊያመጣው ከሚችለው አደጋ ማስጠንቀቅ፤
10. ሴት ልጅ የወንድ ተከታይ ስለ መሆኗ ራሷን የማትችል ስለመሆኗ፤
11. ሀፍረተ ገላን መግለፅ ክልክል ስለመሆኑ፤
12. አባታችን አደም ነብይ ስለመሆናቸው፤
13. በቁርኣን አምነው ለተገበሩት ሰዎች አላህ የገባው መልካም ቃል ኪዳን፤
14. በቁርኣን የማይሰሩ ሰዎች በዱንያም ሆነ በአኼራ የሚጠብቃቸውን ሰቆቃ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የጧሃ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (21)
# የነብያት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልአንቢያ)

سُورَةُ الأَنبِيَاءِ

## የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (112) ናቸው።
## የሱረቱ አል አንቢያ መግቢያ

ይህን የተለየ ስም የተሰጠበት ምክንያት የ (18) ነብያት ታሪክ ስለተተነተነበት ነው። ከሐሚሞች መካከል ሱጁድ ያለበት በመሆኑ ነው።

ከሓዲያን ቢዘነጉትም የትንሳኤን ቀን መቅረብ ያስተምራል። ከሓዲያን «ሰው ነብይ አይሆንም፤ ቁርኣንንም ድግምት ነው። ዘፈን ነው፤ ቅዠት ነው፤ እያሉ ልዩ ልዩ ስም እየሰጡ የነበሩ መሆናቸውን ያብራራል ሆኖም ማስፈራሪያውና ማስረጃው በአጠገባቸው ነበር። ከሓዲያን ቢዘነጉትም ነብያት የትንሳኤ መልዕክተኞች ሰዎች እንጂ ሌላ አልነበሩም። ከሙሐመድ በፊትም የነበሩት ነብያት ልክ እንደ ነብዩ (ﷺ) ከሓዲያን ያስተባብሏቸው እንደነበርና አላህ መንደሮቻቸውን ሳትቀር እንዳጠፋባቸው ሁሉ ቁረይሾችም በዚሁ ተግባራቸው ላይ ከቀጠሉ እጣቸው ይኸው እንደሆነ በማስጠንቀቅ ነብዩን ያፅናናል። በሰማይና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የአላህ መሆኑንና መላኢኮችም ያለ መሰላቸት እንደሚያጠሩት፤ የሰማይና የምድር አለመበላሸት የፈጣሪያቸውን አንድነት ያመለክታል። በሁለት ኃያላን መንግስታት ቢፈጠሩ ምላሹ ምን ይሆን እንደነበር ግልፅ ነው። ነብያት ሁሉ የአላህን ብቸኛ አምላክነት በማስተማር ላይ እንደተላኩ አላህን ልጅ አለው ያለ ሁሉ የጀሀነም እንደሆነ ያስረዳል። አላህ የፍጥረታትን ግዙፍነት ከማስረዳቱም በተጨማሪ ሰዎችን እንደሚጠብቃቸውና ከሀዲዎች በገሀነም ምን እንደሚጠብቃቸው ያብራራል። ከዚያ ነብዩ ሙሳና ወንድማቸው ሀሩን ከፊርዐውን ጋር፤ ነብዩ ኢብራሂም ከተላኩባቸው ሰዎች ጋር ያሳለፉትን ታሪክ ይተርካል። ነብዩ ሉጥ ከሰዎቻቸው ጋር፤ ነብዩ ኑህም ከህዝቦቻቸው ጋር ያሳለፉትን አስገራሚ ታሪክ ከማውሳቷም በተጨማሪም፤ የነብዩ ሱለይማን፤ የነብዩ ዳውድ፤ የነብዩ ኢስማኤል፤ የነብዩ ኢድሪስ፤ የነብዩ ዙልኪፍል፤ የነብዩ ዩኑስ የመርየምና የልጇን (عليه السلام) ታሪክ ከማውሳቱም በላይ ያዕጁጅና መዕጁጅ ስለ ሚባሉት ሰዎችም በአጭሩ ይዘግባል። በመጨረሻም የመልካም ስራን ጥቅም፤ የአማኞችን ምንዳ፤ የነብዩ ተልዕኮ ያበረከተው ራህመት መሆኑን በማውሳት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱقۡتَرَبَ لِلنَّاسِ حِسَابُهُمۡ وَهُمۡ فِي غَفۡلَةٖ مُّعۡرِضُونَ ﴿١﴾ مَا يَأۡتِيهِم مِّن ذِكۡرٖ مِّن رَّبِّهِم مُّحۡدَثٍ
إِلَّا ٱسۡتَمَعُوهُ وَهُمۡ يَلۡعَبُونَ ﴿٢﴾ لَاهِيَةٗ قُلُوبُهُمۡۗ وَأَسَرُّواْ ٱلنَّجۡوَى ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ هَلۡ هَٰذَآ
إِلَّا بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡۖ أَفَتَأۡتُونَ ٱلسِّحۡرَ وَأَنتُمۡ تُبۡصِرُونَ ﴿٣﴾ قَالَ رَبِّي يَعۡلَمُ ٱلۡقَوۡلَ فِي ٱلسَّمَآءِ
وَٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٤﴾

**1-4.** ለሰዎች እነርሱ በዝንጋታ ውስጥ (መሰናዳትን) የተው ሆነው ሳሉ ምርመራቸው ቀረበ። ከጌታቸው አዲስ የተወረደ ቁርኣን አይመጣላቸውም። እነርሱ የሚያላግጡበት ሆነው የሚያዳምጡት ቢሆኑ እንጂ። ልቦቻቸው ዝንጉዎች ሆነው (የሚያዳምጡት ቢሆኑ እንጂ)። እነዚያም የበደሉት ሰዎች መንሾካሾክን ደበቁ። ይህ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ ነውን? እናንተም የምታዩ ስትሆኑ ድግምትን ለመቀበል ትመጣላችሁን? አሉ። (ሙሐመድም) ጌታዬ ቃልን ሁሉ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለ ሲሆን ያውቃል። እርሱም ሰሚውና አዋቂው ነው አለ።

بَلۡ قَالُوٓاْ أَضۡغَٰثُ أَحۡلَٰمِۭ بَلِ ٱفۡتَرَىٰهُ بَلۡ هُوَ شَاعِرٞ فَلۡيَأۡتِنَا بِـَٔايَةٖ كَمَآ أُرۡسِلَ ٱلۡأَوَّلُونَ ﴿٥﴾

**5.** በእውነቱ ቁርኣኑ የሕልሞች ቅዠቶች ነው። ይልቁንም ቀጠፈው እንዲያውም እርሱ ቅኔን ገጣሚ ነው። የቀድሞዎቹ እንደ ተላኩ መልዕክተኛ ከሆነ በተዐምር ይምጣብን አሉ።

مَآ ءَامَنَتۡ قَبۡلَهُم مِّن قَرۡيَةٍ أَهۡلَكۡنَٰهَآۖ أَفَهُمۡ يُؤۡمِنُونَ ﴿٦﴾ وَمَآ أَرۡسَلۡنَا قَبۡلَكَ إِلَّا رِجَالٗا نُّوحِيٓ
إِلَيۡهِمۡۖ فَسۡـَٔلُوٓاْ أَهۡلَ ٱلذِّكۡرِ إِن كُنتُمۡ لَا تَعۡلَمُونَ ﴿٧﴾ وَمَا جَعَلۡنَٰهُمۡ جَسَدٗا لَّا يَأۡكُلُونَ ٱلطَّعَامَ
وَمَا كَانُواْ خَٰلِدِينَ ﴿٨﴾ ثُمَّ صَدَقۡنَٰهُمُ ٱلۡوَعۡدَ فَأَنجَيۡنَٰهُمۡ وَمَن نَّشَآءُ وَأَهۡلَكۡنَا ٱلۡمُسۡرِفِينَ ﴿٩﴾

**6-9.** ከእነርሱ በፊት ያጠፋናት ከተማ አላመነችም። ታዲያ እነርሱ ያምናሉን?* (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተም በፊት ወንድ ሆነው የምናወርድላቸው የሆኑ ሰዎችን እንጂ ሌላን አላክንም። የማታውቁ ከሆናችሁ የመጽሐፉን ባለቤቶች ጠይቁ። ምግብን የማይበሉ አካልም

አላደረግናቸውም። ዘውታሪዎችም አልነበሩም። ከዚያ ቀጠሮን ሞላንላቸውና እነርሱንና የምንሻውን ሰው አዳንናቸውም። ወሰን አላፊዎችንም አጠፋን።

✷ ከነብያት ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- መኮች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው «የምትለው እውነት ከሆነና እንድናምንልህ የምትፈልግ ከሆነ የሶፋን ጋራ ወርቅ አድርግልን» ብለው ሲጠይቁ መልአኩ ጅብሪል መጥቶ «ሰዎች የጠየቁት ከተደረገ እና ካላመኑ ጊዜ አይሰጣቸውም። ከፈለክ ግን ጊዜ ሰጥተሃቸው በፍቃደኝነት እንዲያምኑህ ይደረግ» ባላቸው ጊዜ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

لَقَدۡ أَنزَلۡنَآ إِلَيۡكُمۡ كِتَٰبٗا فِيهِ ذِكۡرُكُمۡۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴿١٠﴾

**10.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ክብራችሁ እሱን በመከተል ብቻ የሆነበትን መጽሐፍ ወደ እናንተ በእርግጥ አወረድን፤ አታውቁምን?

وَكَمۡ قَصَمۡنَا مِن قَرۡيَةٖ كَانَتۡ ظَالِمَةٗ وَأَنشَأۡنَا بَعۡدَهَا قَوۡمًا ءَاخَرِينَ ﴿١١﴾ فَلَمَّآ أَحَسُّواْ بَأۡسَنَآ إِذَا هُم
مِّنۡهَا يَرۡكُضُونَ ﴿١٢﴾ لَا تَرۡكُضُواْ وَٱرۡجِعُوٓاْ إِلَىٰ مَآ أُتۡرِفۡتُمۡ فِيهِ وَمَسَٰكِنِكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تُسۡـَٔلُونَ ﴿١٣﴾
قَالُواْ يَٰوَيۡلَنَآ إِنَّا كُنَّا ظَٰلِمِينَ ﴿١٤﴾ فَمَا زَالَت تِّلۡكَ دَعۡوَىٰهُمۡ حَتَّىٰ جَعَلۡنَٰهُمۡ حَصِيدًا خَٰمِدِينَ ﴿١٥﴾

**11-15.** በዳይም ከነበረች ከተማ ያጠፉናትና ከኋላዋም ሌሎችን ህዝቦች ያስገኘነው ብዙ ናት። ቅጣታችንም በተሰማቸው ጊዜ እነርሱ ወዲያውኑ ከርሷ ለመሸሽ ይገሰግሳሉ። አትገስግሱ፤ ትጠየቁም ይሆናልና በእርሱ ወደ ተቀማጠላችሁበት ፀጋ ወደ መኖሪያዎቻችሁም ተመለሱ ይባላሉ። ዋ! ጥፋታችን እኛ በእርግጥ በዳዮች ነበርን ይላሉ። የታጨዱ ሬሳዎችም እስካደረግናቸው ድረስ ይህቺ ጥሪያቸው ከመሆን አልተወገደችም።

وَمَا خَلَقۡنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَا لَٰعِبِينَ ﴿١٦﴾ لَوۡ أَرَدۡنَآ أَن نَّتَّخِذَ لَهۡوٗا لَّٱتَّخَذۡنَٰهُ مِن
لَّدُنَّآ إِن كُنَّا فَٰعِلِينَ ﴿١٧﴾ بَلۡ نَقۡذِفُ بِٱلۡحَقِّ عَلَى ٱلۡبَٰطِلِ فَيَدۡمَغُهُۥ فَإِذَا هُوَ زَاهِقٞۚ وَلَكُمُ
ٱلۡوَيۡلُ مِمَّا تَصِفُونَ ﴿١٨﴾

**16-18.** ሰማይንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ ቀላጆች ሆነን አልፈጠርንም። መጫዎቻን ሚስትን ልጅን ልንይዝ በሻን ኖሮ ከኛ ዘንድ በያዝነው ነበር ግን ሰሪዎች አይደለንም። በእርግጥ እውነትን በውሸት ላይ እንጥላለን። አንጎሉን ያፈርሰዋልም። ወዲያዉም እርሱ ጠፊ ነው። ለእናንተም ከዚያ ሚስትና ልጅ አለው በማለት ከምትመጥኑት ነገር ብርቱ ቅጣት አላችሁ። (ወዮላችሁ)።

وَلَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَمَنۡ عِندَهُۥ لَا يَسۡتَكۡبِرُونَ عَنۡ عِبَادَتِهِۦ وَلَا يَسۡتَحۡسِرُونَ ١٩
يُسَبِّحُونَ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ لَا يَفۡتُرُونَ ٢٠

**19-20.** በሰማያትና በምድር ዉስጥ ያለው ሁሉም የእርሱ ነው። እርሱ ዘንድ ያሉትም መላእክት እርሱን ከመገዛት አይኮሩም አይሰለቹምም። በሌሊትና በቀንም ያጠሩታል። አያርፉም።

أَمِ ٱتَّخَذُوٓاْ ءَالِهَةٗ مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ هُمۡ يُنشِرُونَ ٢١ لَوۡ كَانَ فِيهِمَآ ءَالِهَةٌ إِلَّا ٱللَّهُ لَفَسَدَتَاۚ
فَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ رَبِّ ٱلۡعَرۡشِ عَمَّا يَصِفُونَ ٢٢

**21-22.** ይልቁንም ከምድር የሆኑን እነርሱ ሙታንን የሚያስነሱን አማልክት ያዙን? (የለም)። በሁለቱ (በሰማያትና በምድር ውስጥ) ከአላህ ሌላ አማልክት በነበሩ ኖሮ ሁለቱም በተበላሹ ነበር። የዐርሹ ጌታ አላህም ከሚሉት ሁሉ ጠራ።

لَا يُسۡـَٔلُ عَمَّا يَفۡعَلُ وَهُمۡ يُسۡـَٔلُونَ ٢٣

**23.** ከሚሰራው ሁሉ አይጠየቅም። እነርሱ ፍጥረቶቹ ግን ይጠየቃሉ።

أَمِ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةٗۖ قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡۖ هَٰذَا ذِكۡرُ مَن مَّعِيَ وَذِكۡرُ مَن قَبۡلِيۚ
بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ٱلۡحَقَّۖ فَهُم مُّعۡرِضُونَ ٢٤

**24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይልቁንም ከርሱ ሌላ አማልክትን ያዙን? አስረጃችሁን አምጡ። ይህ ቁርአን እኔ ዘንድ ያለው ህዝብ መገሰጫ ከኔ በፊትም የነበሩት ህዝቦች መገሠጫ ነው በላቸው። እንዲያውም አብዛኞቻቸው እውነቱን አያውቁም። ስለዚህ እነርሱ እንቢተኞች ናቸው።

وَمَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ مِن رَّسُولٍ إِلَّا نُوحِيٓ إِلَيۡهِ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنَا۠ فَٱعۡبُدُونِ ٢٥

**25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊትም እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደ እርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልዕክተኛ አንድንም አላክንም።*

* ቁርኣን ተውራትና ሌሎችም ከአላህ የመጡ መፅሐፍቶች የአላህን አንድነት በማስረዳት አንድ አቋም ያላቸው በመሆናቸው ሁሉም የሚስማሙበት ወሳኝ ነገር ቢኖር ማንም ነገር እራሱን አይፈጥርም በሚለው ላይ ነው። ስለዚህ ሰው እንኳን በጣም አዋቂ ነኝ ባይ የሆነው ይህን ሁሉ

እውቀት የተሰጠውና ከፍተኛ እውቀት ላይ መድረሱ የሚነገርለት እንኳን ሳይቀር እራሱን አልፈጠረም እኔም እፈጥራለሁ ብሎ አያውቅም ታዲያ ይህ ሁሉ ፍጡር እራሱን ካልፈጠረ ፈጣሪው አላህ ብቻ ነው። ለዚህ ነው አላህ (35-36) ፈታኝ ጥያቄዎችን በማቅረብ የእሱን ፈጣሪነት ከመቀበል ሌላ አማራጭ እንደሌለ በግልፅ ያስተማረው። የዘመኑ ቀብር አምላኪዎችም ቢሆኑ ቀብሩም ሆነ ዶሪሁ ዝናብ አመጣ፤ ቡቃያ አበቀለ፤ አስታመመ፤ ገደለ፤ ወይም አዳነ አይሉም። ሁሉም የጣኦት አምላኪዎች የሚሉት ቢኖር እነዚህ የምናመልካቸው ባዕድ አማልዕክት በሙሉ ወደ ዋናው (ታላቁ) ጌታ አቃራቢዎች ናቸው ነው የሚሉት። አላህ በሐዲሰል ቁድስ «እኔ ከሰዎችና ከጋኔሎች ጋር አስገራሚ ዜና አለን። እኔ እየፈጠርኩ የሚመለከው ግን ሌላው ነው። እኔ እየመገብኩ የሚመሰገነው ሌላኛው» ብሏል። (የእስሳት- ምእራፍ፡ 136)

በአጠቃላይ ከአላህ ሌላ የሆኑት ፍጡሮች አላዋቂዎች የአምላክነት ባህሪ ቢሰጧቸው እነሱ ግን የአምላክነት ባህሪ የላቸውም። የተለመኑትን ነገር መስጠት አይችሉም . (ፋጢር፡ 14) የአምላክን መብዛት ከሚቃረኑ ነገሮች ሁለት ነገሮች እኩል አዛዥ እኩል ስልጣን ያላቸው ሆነው መኖር ለአምላኪው ማህበራዊ ኑሮዎች እራሱ አስቸጋሪ መሆኑ ነው። . 38 ዙመር 19 ሒጅር 36-38።

وَقَالُواْ ٱتَّخَذَ ٱلرَّحۡمَٰنُ وَلَدٗاۗ سُبۡحَٰنَهُۥۚ بَلۡ عِبَادٞ مُّكۡرَمُونَ ﴿٢٦﴾ لَا يَسۡبِقُونَهُۥ بِٱلۡقَوۡلِ وَهُم
بِأَمۡرِهِۦ يَعۡمَلُونَ ﴿٢٧﴾ يَعۡلَمُ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُمۡ وَلَا يَشۡفَعُونَ إِلَّا لِمَنِ ٱرۡتَضَىٰ وَهُم
مِّنۡ خَشۡيَتِهِۦ مُشۡفِقُونَ ﴿٢٨﴾ ۞وَمَن يَقُلۡ مِنۡهُمۡ إِنِّيٓ إِلَٰهٞ مِّن دُونِهِۦ فَذَٰلِكَ نَجۡزِيهِ جَهَنَّمَۚ
كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢٩﴾

**26-29.** አረሕማንም ከመላእክት መካከል ልጅን ያዘ አሉ። ጥራት ተገባው፤ አይደለም መላእክት የተከበሩ ባሮች ብቻ ናቸው። በንግግር አይቀድሙትም (ያላለውን አይሉም) ያዘዘውን ይፈፅማሉ፤ በፊታቸው ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ያውቃል። ለወደደው ሰው እንጂ ለሌላው አያማልዱም። እነርሱም እርሱን ከመፍራታቸው የተነሳ ተጨናቂዎች ናቸው። ከእነርሱም እኔ ከእርሱ ሌላ አምላክ ነኝ የሚል ያንን ገሀነምን እንመነዳዋለን፤ እንደዚሁ በዳዮችን እንመነዳለን።

أَوَلَمۡ يَرَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَنَّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ كَانَتَا رَتۡقٗا فَفَتَقۡنَٰهُمَاۖ وَجَعَلۡنَا مِنَ ٱلۡمَآءِ
كُلَّ شَيۡءٍ حَيٍّۚ أَفَلَا يُؤۡمِنُونَ ﴿٣٠﴾ وَجَعَلۡنَا فِي ٱلۡأَرۡضِ رَوَٰسِيَ أَن تَمِيدَ بِهِمۡ وَجَعَلۡنَا فِيهَا
فِجَاجٗا سُبُلٗا لَّعَلَّهُمۡ يَهۡتَدُونَ ﴿٣١﴾ وَجَعَلۡنَا ٱلسَّمَآءَ سَقۡفٗا مَّحۡفُوظٗاۖ وَهُمۡ عَنۡ ءَايَٰتِهَا
مُعۡرِضُونَ ﴿٣٢﴾ وَهُوَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ وَٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ كُلّٞ فِي فَلَكٖ يَسۡبَحُونَ ﴿٣٣﴾

**30-33.** እነዚያም በአላህ የካዱ ሰዎች ሰማያትና ምድር የተጣበቁ የነበሩና የለያየናቸው መሆናችንን አያውቁምን? ህያው የሆነንም ነገር ሁሉ ከውሃ ፈጠርን አያምኑምን? በምድርም ውስጥ በእነርሱ እንዳታረገርግ ጋራዎችን አደረግን። ይመሩም ዘንድ በእርሷ ውስጥ ሰፋፊ መንገዶችን አደረግን። ሰማይንም ከመውደቅ የተጠበቀ ጣራ አደረግን። እነርሱ ግን ከተአምራቶቹ ዘንጊዎች ናቸው። እርሱም ያ ሌሊትንና ቀንን ፀሐይንና ጨረቃንም የፈጠረ ነው፤ ሁሉም በፈለካቸው ውስጥ ይዋኛሉ።

**ከነብያት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-33) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሓዲያን የነበሩበትን ባህሪያት መጠቆም፤
2. አጋሪዎች ስለ ወህይና ስለ ነብዩ (ﷺ) የነበራቸው ጭንቀትና ጥርጣሬ፤
3. ስለ ትንሳኤ ቀን መቅረብ፤
4. ተዐምር ማየት ለሰው ልጆች እምነት ምክንያት ሆኖ እንደማያውቅ፤
5. ነብያት ሰዎች እንደሆኑ፤
6. ሰዎች የማያውቁትን ነገር ከአዋቂዎች ጠይቀው መረዳት እንዳለባቸው፤
7. በሁሉም ነገር ላይ ማባከንን ማውገዝ፤
8. ቁርኣን አላህ የሚወሳበት መፅሐፍ ስለመሆኑ፤
9. ግፍ የተባለን ሁሉ ማውገዝ፤
10. ጥፋተኞች ቅጣት ከደረሰባቸው በኋላ ተውበት ቢያደርጉ ተቀባይነት እንደሌላቸው፤
11. ቅጣትን ማየትና የቅጣት ክብደት የሰዎችን አዕምሮ እንደሚያስት የሚናገሩት እስካለማወቅ እንደሚደርሱ፤
12. አላህ ከሚስትም ሆነ ከልጅ የፀዳ ስለመሆኑ፤
13. የቁርኣን ማስረጃነት ከማስረጃዎች ሁሉ የበላይ ስለመሆኑ፤
14. ሎጂካዊ ማስረጃዎችን ማቅረብ ከመውደዱ በላይ አማራጭ የሌለው እንደሆነ፤
15. አላህ ከሁሉም ነገር የተብቃቃ ስለ መሆኑ፤
16. መላኢኮች በአምልኮ ተግባር ላይ ያላቸውን ባህሪ፤
17. አምላክ ማለት የሚፈጥር የሚመግብ ህያው የሚያደርግ ስለ መሆኑ፤
18. አለም በአንድ ስርዓት መመራቷ ስርአት አውጪው አንዱና ኃያሉ ጌታ አላህ መሆኑ እንደሚያሳይ፤
19. ማጋራት በትክክለኛ አዕምሮም ብቻ ቢሆን ተቀባይነት የሌለው ፉርሽ ነገር መሆኑን፤
20. አላህ ልጅ አለው የሚለውን አባባል ማውገዝ፤
21. መላኢኮች የአላህ አገልጋይ ስለመሆናቸው
22. አጋሪዎች መላኢኮች ይሸመግሉናል ማለታቸው ስህተት እንደሆነ፤
23. በቂያማ ቀን ሽምግልና ያለና የሚሸመግለው ከአላህ ዘንድ የተፈቀደለት ሰው ሲሆንና የሚሸመግልለትም ከሺርክ የፀዳ መሆኑን፤
24. የአላህ ችሎታና እውቀት እንዲሁም ጥበቡን በግልፅ ማየት፤
25. ጋራ የመፍጠሩ ምክንያትን ምን እንደሆነ መግለፅ፤
26. የአላህን ተዐምር አለማስተዋል ለብዙ ሰዎች ስህተትና ወንጀል ምክንያት ስለ መሆኑ እንማራለን።

وَمَا جَعَلْنَا لِبَشَرٍ مِّن قَبْلِكَ ٱلْخُلْدَ ۖ أَفَإِي۟ن مِّتَّ فَهُمُ ٱلْخَٰلِدُونَ ﴿٣٤﴾ كُلُّ نَفْسٍ ذَآئِقَةُ ٱلْمَوْتِ ۗ
وَنَبْلُوكُم بِٱلشَّرِّ وَٱلْخَيْرِ فِتْنَةً ۖ وَإِلَيْنَا تُرْجَعُونَ ﴿٣٥﴾

**34-35.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት ለማንም ሰው ዘለዓለም መኖርን አላደረግንም። ታዲያ ብትሞት እነርሱ ዘውታሪዎች ናቸውን? ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት። ለመፈተንም በክፉም በበጎም እንሞክራችኋለን፤ ወደኛም ትመለሳላችሁ።

ከነብያት ምዕራፍ (34) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) እንደሚሞቱ ሲነገራቸው ጌታዬ ሆይ ለሕዝቦቼ ማን አላቸው በማለት ሲጠይቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)።

وَإِذَا رَءَاكَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ إِن يَتَّخِذُونَكَ إِلَّا هُزُوًا أَهَٰذَا ٱلَّذِى يَذْكُرُ ءَالِهَتَكُمْ وَهُم بِذِكْرِ
ٱلرَّحْمَٰنِ هُمْ كَٰفِرُونَ ﴿٣٦﴾

**36.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያም የካዱት ሰዎች ባዩህ ጊዜ መሳለቂያ አድርገው እንጂ አይዙህም እነርሱ በአልረህማን መወሳት እነርሱ ከሓዲዎች ሲሆኑ ያ አማልክቶቻችሁን በክፉ የሚያነሳቸው ይህ ነውን? ይላሉ።

ከነብያት ምዕራፍ (36) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በአቡ ጀህልና በአቡ ሱፍያን አጠገብ እያለፉ ሳሉ እነሱ እየተወያዩ ባሉበት ስለ ነበር አቡጀህል ሲያያቸው ሳቀና ለአቡ ሱፍያንም የአብድመናፍ ነቢይ ይህኮ ነው አለ። አቡሱፍያንም ተቆጥቶ ለአቡጀህል የአብዱመናፍ ቤተሰቦች ነቢይ እንዲኖራቸው ትቃወማላችሁ ማለቱን ነብዩ ስለሰሙ ወደ አቡጀህል በመመለስ አስፈራርተውት አንተ እኮ ቃሉን ያፈረሱትን ሰዎች ያጋጠማቸውን ነገር እስከሚደርስብህ አታርፍም ስላሉት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

خُلِقَ ٱلْإِنسَٰنُ مِنْ عَجَلٍ ۚ سَأُو۟رِيكُمْ ءَايَٰتِى فَلَا تَسْتَعْجِلُونِ ﴿٣٧﴾ وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا
ٱلْوَعْدُ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٣٨﴾ لَوْ يَعْلَمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ حِينَ لَا يَكُفُّونَ عَن وُجُوهِهِمُ
ٱلنَّارَ وَلَا عَن ظُهُورِهِمْ وَلَا هُمْ يُنصَرُونَ ﴿٣٩﴾ بَلْ تَأْتِيهِم بَغْتَةً فَتَبْهَتُهُمْ فَلَا يَسْتَطِيعُونَ
رَدَّهَا وَلَا هُمْ يُنظَرُونَ ﴿٤٠﴾

**37-40.** ሰው ችኳይ ሆኖ ተፈጠረ። ታምራቶቼን በእርግጥ አሳያችኋለሁና አታቻኩሉኝ። ይህ ቀጠሮም መቼ ነው? እውነተኞች ከሆናችሁ አምጡት ይላሉ። እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ከፊቶቻቸውና ከጀርባቸው ላይ እሳትን የማይከለክሉበትን እነርሱም የማይረዳዱበትን ጊዜ ቢያውቁ ኖሮ (ይህንን አይሉም ነበር)። ይልቁንም ሰዓቲቱ በድንገት ትመጣቸዋለች። ታስደነግጣቸዋለችም። መመለሷንም አይችሉም። እነርሱም አይቆዩም።

وَلَقَدِ ٱسۡتُهۡزِئَ بِرُسُلٖ مِّن قَبۡلِكَ فَحَاقَ بِٱلَّذِينَ سَخِرُواْ مِنۡهُم مَّا كَانُواْ بِهِۦ يَسۡتَهۡزِءُونَ ﴿٤١﴾

**41.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊትም የነበሩት መልዕክተኞች በእርግጥ ተቀለደባቸው በእነዚያ ከእነርሱ ይቀልዱ በነበሩት በእርሱ ይሳለቁበት የነበሩት ቅጣት ሰፈረባቸው።

قُلۡ مَن يَكۡلَؤُكُم بِٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ مِنَ ٱلرَّحۡمَٰنِۚ بَلۡ هُمۡ عَن ذِكۡرِ رَبِّهِم مُّعۡرِضُونَ ﴿٤٢﴾
أَمۡ لَهُمۡ ءَالِهَةٞ تَمۡنَعُهُم مِّن دُونِنَاۚ لَا يَسۡتَطِيعُونَ نَصۡرَ أَنفُسِهِمۡ وَلَا هُم مِّنَّا يُصۡحَبُونَ ﴿٤٣﴾
بَلۡ مَتَّعۡنَا هَٰٓؤُلَآءِ وَءَابَآءَهُمۡ حَتَّىٰ طَالَ عَلَيۡهِمُ ٱلۡعُمُرُۗ أَفَلَا يَرَوۡنَ أَنَّا نَأۡتِي ٱلۡأَرۡضَ نَنقُصُهَا
مِنۡ أَطۡرَافِهَآۚ أَفَهُمُ ٱلۡغَٰلِبُونَ ﴿٤٤﴾

**42-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአልረህማን ቅጣት በሌሊትና በቀን የሚጠብቃችሁ ማነው? በላቸው። በእውነቱ እነርሱ ከጌታቸው ግሣጼ ከቁርኣን ዘንጊዎች ናቸው። ለእነርሱ ከእኛ ሌላ የምትከላከልላቸው አማልዕክት አለቻቸውን? ነፍሶቻቸውን መርዳትን አይችሉም። እነርሱም (ከሓዲያን) ከእኛ አይጠብቁም። በእውነትም እነዚህንና አባቶቻቸውን በእነርሱ ላይ ዕድሜ እስከ ረዘመባቸው ድረስ አጣቀምናቸው። ተታለሉም እኛ ምድርን ከጫፎችዋ የምናጎድላት ሆነን ስንመጣባት አያዩምን እነርሱ አሸናፊዎች ናቸውን?

قُلۡ إِنَّمَآ أُنذِرُكُم بِٱلۡوَحۡيِۚ وَلَا يَسۡمَعُ ٱلصُّمُّ ٱلدُّعَآءَ إِذَا مَا يُنذَرُونَ ﴿٤٥﴾ وَلَئِن مَّسَّتۡهُمۡ
نَفۡحَةٞ مِّنۡ عَذَابِ رَبِّكَ لَيَقُولُنَّ يَٰوَيۡلَنَآ إِنَّا كُنَّا ظَٰلِمِينَ ﴿٤٦﴾

**45-46.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የማስፈራራችሁ በተወረድልኝ ብቻ ነው ግን ደንቆሮዎች በሚስፈራሩበት ጊዜ ጥሪን አይሰሙም በላቸው። ከጌታህ ቅጣትም ወላፈን ብትነካቸው ዋ፣ ጥፋታችን እኛ በዳዮች ነበርን ይላሉ።

وَنَضَعُ ٱلۡمَوَٰزِينَ ٱلۡقِسۡطَ لِيَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ فَلَا تُظۡلَمُ نَفۡسٞ شَيۡـٔٗاۖ وَإِن كَانَ مِثۡقَالَ حَبَّةٖ مِّنۡ
خَرۡدَلٍ أَتَيۡنَا بِهَاۗ وَكَفَىٰ بِنَا حَٰسِبِينَ ﴿٤٧﴾

**47.** በትንሳኤ ቀን ትክክለኛ ሚዛኖችን እናቆማለን። ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም። ስራው የሰናፍጭ ቅንጣት ያክል ቢሆንም እርሷን እናመጣታለን። ተቆጣጣሪዎችም በእኛ በቃ።

**ከነብያት ምዕራፍ ከአንቀፅ (34-47) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኽድር ዘላለማዊ ህያው ናቸው እየተባለ የሚወራውን በግልፅ ማውገዝ፤
2. ደግና መጥፎውን መፍጠሩ ለፈተና ስለመሆኑ፤
3. ከሓዲያን በነብዩ (ﷺ) ላይ ያደርሱት የነበረው መከራና ስቃይ፤
4. የሰው ልጅ በተፈጥሮ ችኩል እንደሆነ፤
5. ቂያማ በድንገት እንደምትመጣ፤
6. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
7. ነብዩን (ﷺ) ማፅናናት፤
8. የአጋሪዎች አማልክት አምላኪዎቻቸውን መርዳት እንደማይችሉ፤
9. ከሓዲያን በክህደት ላይ ሙጥኝ ያለበት ምክንያት ቁርአንን በጥሞና በማጤናቸው መሆኑን፤
10. ዘላለማዊ ህያው ናቸው እየተባለ የሚወራው በግልፅ ማውገዝ፤
11. ደግና መጥፎውን መፍጠሩ ለፈተና መሆኑን፤
12. የእድሜ መርዘምና የሲሳይ መብዛት የሰውን ልጅ ሊያሞኘው እንደሚችል፤
13. አንድን ነገር የወደደ ሰው ጥፋቱን ሊያይ እንደማይችል፤
14. የሰው ልጅ ደካማና ከአላህ የሚመጣበትን አነስተኛ ቅጣት እንኳን መሸከም የማይችል ስለ መሆኑ፤
15. በአላህ ፊት ለምርመራ መቅረብ ያለ መሆኑን፤

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَىٰ وَهَٰرُونَ ٱلۡفُرۡقَانَ وَضِيَآءٗ وَذِكۡرٗا لِّلۡمُتَّقِينَ ﴿٤٨﴾ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُم
بِٱلۡغَيۡبِ وَهُم مِّنَ ٱلسَّاعَةِ مُشۡفِقُونَ ﴿٤٩﴾ وَهَٰذَا ذِكۡرٞ مُّبَارَكٌ أَنزَلۡنَٰهُۚ أَفَأَنتُمۡ لَهُۥ مُنكِرُونَ ﴿٥٠﴾

**48-50.** ለሙሳና ለሃሩንም እውነትንና ውሸትን የሚለይን ብርሃንን ለጥንቁቆችም መገሰጫን በእርግጥ ሰጠናቸው። ለእነዚያ ጌታቸውን በሩቅ ለሚፈሩት እነርሱም ከሰዓቲቱ ተጨናቂዎች ለሆኑት (መገሰጫን) ሰጠን። ይህ ቁርአን ነው። ብሩክም መገሰጫ ነው። አወረድነውምም ታዲያ እናንተ ለእርሱ ከሓዲዎች ናችሁን?

۞وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَآ إِبۡرَٰهِيمَ رُشۡدَهُۥ مِن قَبۡلُ وَكُنَّا بِهِۦ عَٰلِمِينَ ﴿٥١﴾ إِذۡ قَالَ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦ مَا هَٰذِهِ
ٱلتَّمَاثِيلُ ٱلَّتِيٓ أَنتُمۡ لَهَا عَٰكِفُونَ ﴿٥٢﴾ قَالُواْ وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا لَهَا عَٰبِدِينَ ﴿٥٣﴾ قَالَ لَقَدۡ كُنتُمۡ
أَنتُمۡ وَءَابَآؤُكُمۡ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ﴿٥٤﴾ قَالُوٓاْ أَجِئۡتَنَا بِٱلۡحَقِّ أَمۡ أَنتَ مِنَ ٱللَّٰعِبِينَ ﴿٥٥﴾ قَالَ بَل
رَّبُّكُمۡ رَبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ ٱلَّذِي فَطَرَهُنَّ وَأَنَا۠ عَلَىٰ ذَٰلِكُم مِّنَ ٱلشَّٰهِدِينَ ﴿٥٦﴾ وَتَٱللَّهِ
لَأَكِيدَنَّ أَصۡنَٰمَكُم بَعۡدَ أَن تُوَلُّواْ مُدۡبِرِينَ ﴿٥٧﴾ فَجَعَلَهُمۡ جُذَٰذًا إِلَّا كَبِيرٗا لَّهُمۡ لَعَلَّهُمۡ
إِلَيۡهِ يَرۡجِعُونَ ﴿٥٨﴾ قَالُواْ مَن فَعَلَ هَٰذَا بِـَٔالِهَتِنَآ إِنَّهُۥ لَمِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٥٩﴾ قَالُواْ سَمِعۡنَا فَتٗى

يَذۡكُرُهُمۡ يُقَالُ لَهُۥٓ إِبۡرَٰهِيمُ ٦٠ قَالُواْ فَأۡتُواْ بِهِۦ عَلَىٰٓ أَعۡيُنِ ٱلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَشۡهَدُونَ ٦١ قَالُوٓاْ
ءَأَنتَ فَعَلۡتَ هَٰذَا بِـَٔالِهَتِنَا يَٰٓإِبۡرَٰهِيمُ ٦٢ قَالَ بَلۡ فَعَلَهُۥ كَبِيرُهُمۡ هَٰذَا فَسۡـَٔلُوهُمۡ إِن كَانُواْ
يَنطِقُونَ ٦٣ فَرَجَعُوٓاْ إِلَىٰٓ أَنفُسِهِمۡ فَقَالُوٓاْ إِنَّكُمۡ أَنتُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٦٤ ثُمَّ نُكِسُواْ عَلَىٰ رُءُوسِهِمۡ
لَقَدۡ عَلِمۡتَ مَا هَٰٓؤُلَآءِ يَنطِقُونَ ٦٥ قَالَ أَفَتَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُكُمۡ شَيۡـٔٗا وَلَا
يَضُرُّكُمۡ ٦٦ أُفّٖ لَّكُمۡ وَلِمَا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ٦٧ قَالُواْ حَرِّقُوهُ وَٱنصُرُوٓاْ
ءَالِهَتَكُمۡ إِن كُنتُمۡ فَٰعِلِينَ ٦٨ قُلۡنَا يَٰنَارُ كُونِي بَرۡدٗا وَسَلَٰمًا عَلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ ٦٩

**51-69.** ለኢብራሂምም ከዚያ በፊት ቅን መንገዱን በእርግጥ ሰጠነው። እኛም በእርሱ ተገቢነት ዐዋቂዎች ነበርን። ለአባቱና ለህዝቦቹ፡- ይህቺ ቅርጻ ቅርጽ ያቺ እናንተ ለእርሷ ተገዢዎች የሆናችሁት ምንድን ናት? ባለ ጊዜ መራነው። አባቶቻችንን ለእርሷ ተገዢዎች ሆነው አገኘን አሉት። እናንተም አባቶቻችሁም በእርግጥ በግልጽ ስህተት ውስጥ ነበራችሁ አላቸው። በምሩ መጣህልን? ወይንስ አንተ ከሚቀልዱት ነህ? አሉት። አይደለም ጌታችሁ የሰማያትና የምድር ጌታ ያ የፈጠራቸው ነው። እኔም በይሃችሁ ላይ ከመስካሪዎች ነኝ አለ። በአላህ እምላለሁ ዟሪዎች ሆናችሁ ከሄዳችሁ በኋላ ጣኦቶቻችሁን ተንኮል እሰራባቸዋለሁ አለ። ዘወር ሲሉ ስብርብሮችም አደረጋቸው። ለእነርሱ የሆነ አንድ ታላቅ ጣዖት ብቻ ሲቀር ወደ እርሱ ይመለሱ ዘንድ (እርሱን ተወው)። በአማልክቶቻችን ይህንን የሰራ ማነው? እርሱ በእርግጥ ከበደለኞች ነው አሉ። ኢብራሂም የሚባል ጎበዝ በመጥፎ ሲያነሳቸው ሰምተናል ተባባሉ። ይመሰክሩበት ዘንድ በሰዎች ዓይን ፊት ላይ አምጡት አሉ። ኢብራሂም ሆይ! በአማልክቶቻችን ይህንን የሰራህ አንተ ነህን? አሉት። አይደለም ይህ ትልቃቸው ሰራው፤ ይናገሩም እንደ ሆነ ጠይቋቸው አለ። ወደ ነፍሶቻቸውም ተመለሱ። እናንተ በመጠየቃችሁ በዳዮች እናንተው ናችሁም ተባባሉ። ከዚያ በራሶቻቸው ላይ ተገለበጡ፤ እነዚህ የሚናገሩ አለመሆናቸውን በእርግጥ ዐውቀሃል (አሉ)። ኢብራሂምም ታዲያ ለእናንተ ብታመልኳቸው ምንም የማይጠቅማችሁንና ባታመልኳቸውም በምንም ነገር የማይጎዳችሁን ጣኡታትን ከአላህ ሌላ ትገዛላችሁን? አላቸው። ኡፍ! ለእናንተም ሆነ ከአላህ ሌላ ለምትገዙት ጣኦታት። አታውቁምን? አለ። ሰሪዎች \ተቆርቋሪዎች\ እንደ ሆናችሁ ኢብራሂምን በእሳት አቃጥሉት አማልክቶቻችሁንም እርዱ አሉ። በእሳት ላይ ጣሉትም። እሳት ሆይ፣ በኢብራሂም ላይ ቀዝቃዛና ሰላም ሁኚ አልን። በእርሱም ተንኮልን አሰቡ። እናም በጣም ከሳሪዎች አደረግናቸው።

وَأَرَادُواْ بِهِۦ كَيْدًا فَجَعَلْنَٰهُمُ ٱلْأَخْسَرِينَ ﴿٧٠﴾ وَنَجَّيْنَٰهُ وَلُوطًا إِلَى ٱلْأَرْضِ ٱلَّتِى
بَٰرَكْنَا فِيهَا لِلْعَٰلَمِينَ ﴿٧١﴾ وَوَهَبْنَا لَهُۥٓ إِسْحَٰقَ وَيَعْقُوبَ نَافِلَةً ۖ وَكُلًّا جَعَلْنَا صَٰلِحِينَ ﴿٧٢﴾
وَجَعَلْنَٰهُمْ أَئِمَّةً يَهْدُونَ بِأَمْرِنَا وَأَوْحَيْنَآ إِلَيْهِمْ فِعْلَ ٱلْخَيْرَٰتِ وَإِقَامَ ٱلصَّلَوٰةِ
وَإِيتَآءَ ٱلزَّكَوٰةِ ۖ وَكَانُواْ لَنَا عَٰبِدِينَ ﴿٧٣﴾

**70-73.** እርሱንና ነብዩ ሉጥንም ወደዚያች በውስጡ ለዓለማት በረከትን ወደ አደረግንባት ምድር በመውሰድ አዳንናቸው፡፡ ለእርሱም ኢስሐቅን ያዕቆብንም ተጨማሪ አድርገን ሰጠነው፡፡ ሁሉንም መልካሞች አደረግን፡፡ በትእዛዛችንም ወደ በጎ ስራ የሚመራ መሪዎች አደረግናቸው፡፡ ወደነሱም መልካም ስራዎችን መስራትን ሶላትንም መስገድን ዘካንም መስጠትን አወረድን፡፡ ለእኛ ተገዢዎች ነበሩ፡፡

وَلُوطًا ءَاتَيْنَٰهُ حُكْمًا وَعِلْمًا وَنَجَّيْنَٰهُ مِنَ ٱلْقَرْيَةِ ٱلَّتِى كَانَت تَّعْمَلُ ٱلْخَبَٰٓئِثَ ۗ إِنَّهُمْ كَانُواْ
قَوْمَ سَوْءٍ فَٰسِقِينَ ﴿٧٤﴾ وَأَدْخَلْنَٰهُ فِى رَحْمَتِنَآ ۖ إِنَّهُۥ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٧٥﴾

**74-75.** ሉጥንም ፍርድንና ዕውቀትን ሰጠነው፡፡ ከዚያችም መጥፎ ስራዎችን ትሰራ ከነበረችው ከተማ አዳንነው፡፡ እነርሱ ክፉ ሰዎች አመፀኞች ነበሩና፡፡ በችሮታችንም ውስጥ አገባነው፡፡ እርሱ ከመልካሞች አንዱ ነውና፡፡

وَنُوحًا إِذْ نَادَىٰ مِن قَبْلُ فَٱسْتَجَبْنَا لَهُۥ فَنَجَّيْنَٰهُ وَأَهْلَهُۥ مِنَ ٱلْكَرْبِ ٱلْعَظِيمِ ﴿٧٦﴾
وَنَصَرْنَٰهُ مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَآ ۚ إِنَّهُمْ كَانُواْ قَوْمَ سَوْءٍ فَأَغْرَقْنَٰهُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٧٧﴾

**76-77.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኑሕንም ከዚያ በፊት ጌታውን በጠራ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)፡፡ ለእርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፤ እርሱንም ቤተሰቦቹንም ከከባድ ጭንቅ አዳን፡፡ ከእነዚያም በታምራቶቻችን ከአስተባበሉት ህዝቦች ተንኮል ጠበቅነው፡፡ እነርሱ ክፉ ህዝቦች አመፀኞች ነበሩና ሁሉንም አሰጠምናቸውም፡፡

وَدَاوُۥدَ وَسُلَيْمَٰنَ إِذْ يَحْكُمَانِ فِى ٱلْحَرْثِ إِذْ نَفَشَتْ فِيهِ غَنَمُ ٱلْقَوْمِ وَكُنَّا لِحُكْمِهِمْ
شَٰهِدِينَ ﴿٧٨﴾ فَفَهَّمْنَٰهَا سُلَيْمَٰنَ ۚ وَكُلًّا ءَاتَيْنَا حُكْمًا وَعِلْمًا ۚ وَسَخَّرْنَا مَعَ دَاوُۥدَ ٱلْجِبَالَ
يُسَبِّحْنَ وَٱلطَّيْرَ ۚ وَكُنَّا فَٰعِلِينَ ﴿٧٩﴾ وَعَلَّمْنَٰهُ صَنْعَةَ لَبُوسٍ لَّكُمْ لِتُحْصِنَكُم مِّنۢ بَأْسِكُمْ ۖ

فَهَلْ أَنتُمْ شَٰكِرُونَ ﴿٨٠﴾ وَلِسُلَيْمَٰنَ ٱلرِّيحَ عَاصِفَةً تَجْرِى بِأَمْرِهِۦٓ إِلَى ٱلْأَرْضِ ٱلَّتِى بَٰرَكْنَا
فِيهَا ۚ وَكُنَّا بِكُلِّ شَىْءٍ عَٰلِمِينَ ﴿٨١﴾ وَمِنَ ٱلشَّيَٰطِينِ مَن يَغُوصُونَ لَهُۥ وَيَعْمَلُونَ عَمَلًا
دُونَ ذَٰلِكَ ۖ وَكُنَّا لَهُمْ حَٰفِظِينَ ﴿٨٢﴾

**78-82.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ዳውድንና ሱለይማንንም በአዝመራው ነገር በሚፈርዱ ጊዜ የህዝቦቸ ፍየሎች ሌሊት በእርሱ ውስጥ በተሰማሩ ጊዜ አስታውስ። ፍርዳቸውንም ዐዋቂዎች ነበርን። ለሱለይማንም ትክክለኛይቱን ፍርድ አሳወቅነው። ለሁሉም ጥበብንና እውቀትን ሰጠን። ተራራዎችን ከዳውድ ጋር የሚያወድሱ ሲሆን ገራን፤ አእዋፍንም እንደዚሁ ገራን ሰሪዎችም ነበርን። የብረት ልብስንም ስራ ለእናንተ ከጦራችሁ ትጠብቃችሁ ዘንድ አስተማርነው። እናንተ አመስጋኞች ናችሁን? ለሱለይማንም ነፍስን በኃይል የምትነፍስ በትእዛዙ ወደዚያች በእርሷ ውስጥ በረከትን ወደ አደረግንባት ምድር (ወደ ሻም) የምትነፈስ ስትሆን (ገራንለት) በነገሩ ሁሉም ዐዋቂዎች ነበርን። ከሰይጣናትም ለእርሱ (ሉልን ለማውጣት) የሚጠልሙንና ከዚያም ሌላ ያለን ስራ የሚሰሩን ገራንለት፤ ለእነርሱም ተጠባባቂዎች ነበርን።

۞ وَأَيُّوبَ إِذْ نَادَىٰ رَبَّهُۥٓ أَنِّى مَسَّنِىَ ٱلضُّرُّ وَأَنتَ أَرْحَمُ ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿٨٣﴾ فَٱسْتَجَبْنَا لَهُۥ فَكَشَفْنَا
مَا بِهِۦ مِن ضُرٍّ ۖ وَءَاتَيْنَٰهُ أَهْلَهُۥ وَمِثْلَهُم مَّعَهُمْ رَحْمَةً مِّنْ عِندِنَا وَذِكْرَىٰ لِلْعَٰبِدِينَ ﴿٨٤﴾

**83-84.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አዩብንም ጌታውን እኔ መከራ አገኘኝ። አንተም ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ ሲል በተጣራ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ለእርሱም ጥሪውን ተቀበልነው፤ ከጉዳትም በእርሱ ላይ የነበረውን ሁሉ አስወገድን። ቤተሰቦችንም ከእነርሱም ጋር መሰላቸውን ከእኛ ዘንድ ለችሮታና ለተገዢዎች ለማስገንዘብ ሰጠነው።

وَإِسْمَٰعِيلَ وَإِدْرِيسَ وَذَا ٱلْكِفْلِ ۖ كُلٌّ مِّنَ ٱلصَّٰبِرِينَ ﴿٨٥﴾ وَأَدْخَلْنَٰهُمْ فِى رَحْمَتِنَآ ۖ
إِنَّهُم مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٨٦﴾

**85-86.** ኢስማዒልንም፣ ኢድሪስንም፣ ዙልኪፍልንም፣ (አስታውስ)፤ ሁሉም ከታጋሾች ናቸው። በችሮታችንም ውስጥ አስገባናቸው፤ እነርሱ ከመልካሞች ናቸውና።

وَذَا ٱلنُّونِ إِذ ذَّهَبَ مُغَٰضِبٗا فَظَنَّ أَن لَّن نَّقۡدِرَ عَلَيۡهِ فَنَادَىٰ فِي ٱلظُّلُمَٰتِ
أَن لَّآ إِلَٰهَ إِلَّآ أَنتَ سُبۡحَٰنَكَ إِنِّي كُنتُ مِنَ ٱلظَّٰلِمِينَ ٨٧ فَٱسۡتَجَبۡنَا لَهُۥ
وَنَجَّيۡنَٰهُ مِنَ ٱلۡغَمِّۚ وَكَذَٰلِكَ نُـۨجِي ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٨٨

**87-88.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዐሳውንም ባለቤት ተቆጥቶ በሄደ ጊዜ የሆነውን አስታውስ። በእርሱም ላይ ፈጽሞ የማንፈርድበት መሆናችንን ጠረጠረ። ዐሳም ዋጠው። በጨለማዎችም ውስጥ ሆነ። ከአንተ በቀር ሌላ አምላክ የለም ጥራት ይገባህ። እኔ በእርግጥ ከበዳዮች ነበርኩ በማለት ተጣራ። ለእርሱም ጥሪውን ተቀበልነው። ከጭንቅም አዳነው። እንደዚሁም ምዕምናንን እናድናለን።

وَزَكَرِيَّآ إِذۡ نَادَىٰ رَبَّهُۥ رَبِّ لَا تَذَرۡنِي فَرۡدٗا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ٨٩ فَٱسۡتَجَبۡنَا لَهُۥ
وَوَهَبۡنَا لَهُۥ يَحۡيَىٰ وَأَصۡلَحۡنَا لَهُۥ زَوۡجَهُۥٓۚ إِنَّهُمۡ كَانُواْ يُسَٰرِعُونَ فِي ٱلۡخَيۡرَٰتِ وَيَدۡعُونَنَا رَغَبٗا
وَرَهَبٗاۖ وَكَانُواْ لَنَا خَٰشِعِينَ ٩٠

**89-90.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ዘከሪያንም ጌታዬ ሆይ! ብቻዬን አትተወኝ። አንተም ከወራሾች ሁሉ በላጭ ነህ ሲል ጌታውን በተጣራ ጊዜ (አስታውስ)። ለእርሱም ጥሪውን ተቀበልነው። ለእርሱም ያህያን ሰጠነው። ለእርሱም ሚስቱን (ለመውለድ) አበጀንለት። እነርሱ በበጎ ስራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ሆነው የሚለምኑንም ነበሩ። ለእኛ ተዋራጆችም ነበሩ።

وَٱلَّتِيٓ أَحۡصَنَتۡ فَرۡجَهَا فَنَفَخۡنَا فِيهَا مِن رُّوحِنَا وَجَعَلۡنَٰهَا وَٱبۡنَهَآ ءَايَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ٩١

**91.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያችንም ብልቷን (ከዝሙት) የጠበቀችውንና በእርሷም ውስጥ ከመንፈሳችን የነፋንባትን እርሷንም ሆነ ልጅዋን ለዓለማት ታዓምር ያደረግናትን (መርየምን አስታውስ)።

إِنَّ هَٰذِهِۦٓ أُمَّتُكُمۡ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ وَأَنَا۠ رَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُونِ ٩٢ وَتَقَطَّعُوٓاْ أَمۡرَهُم بَيۡنَهُمۡۖ كُلٌّ إِلَيۡنَا
رَٰجِعُونَ ٩٣ فَمَن يَعۡمَلۡ مِنَ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَلَا كُفۡرَانَ لِسَعۡيِهِۦ وَإِنَّا لَهُۥ كَٰتِبُونَ ٩٤

**92-94.** እነዚህ ህግጋት አንድ መንገድ ሲሆኑ በእርግጥ የሃይማኖታችሁ ህግጋት ናቸው። እኔም ጌታችሁ ነኝና ተገዙኝ። በሃይማኖታቸውም ነገር

በመካከላቸው ተለያዩ። ሁሉም ወደ እኛ ተመላሾች ናቸው። እርሱ ያመነ ሆኖ ከበጎ ስራዎች ማንኛውንም የሚሰራም ሰው ምንዳውን አይነፍግም፤ እኛም ለእርሱ መዝጋቢዎች ነን።

**ከነብያት ምዕራፍ ምዕራፉ ከአንቀፅ (48-92) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ገደብ የለሹን የአላህን ችሎታ በግልፅ ማሳየት፤
2. በየጊዜ ያሉ ትዕቢተኞች መረጃ ማቅረብ ሲያቅታቸው ኃይልን ጉልበት መጠቀማቸው የተለመደ መሆኑን፤
3. የሻም ምድር የተባረከችና ብዙ ነብያት ከእሷው መላካቸውን፤
4. አላህ ባሮቹንና መልዕክተኞችን በተለያዩ የፈተና አይነቶች እንደሚፈትናቸው፤
5. የአላህ ርህራሄና ረድኤቱ የሰው ልጆች ብቸኛ መጠጊያ መሆኑን፤
6. ነብዩ ዳውድ የሰጡት ውሳኔ ፍትህ ቢሆንም የነብዩ ሱለይማን ደግሞ ጥበብ የተጨመረበት እንደነበረ፤
7. ከፀሎት ስርዓቶች አንዱ በጌታው ላይ አስተያየት አለመስጠትና በመልካም ስሞቹና በውብ ባህሪያቱ መለመን መሆኑን፤
8. ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርጉ ሁሉ ለመመራት ምክንያቶች እንጂ ትክክለኛውን የማስያዙ ስልጣን የአላህ ብቻ መሆኑን፤
9. የሰው ልጅ ሲሳሳት ስህተቱን መቀበልና በስህተቱ ላይ አለመቀጠል ግዴታ መሆኑን፤
10. አዋቂዎች የተሻለ ነገር ሲያገኙ መመለሳቸው፤
11. እመት መርየም ከንፁሃንና ከጥብቅ ሴቶች እንደነበረችና አይሁዶች በእሷ ላይ የቀጠፉትን ቅጥፈት ማጋለጥ፤
12. አላህ የሰውችን መራባት ከወንድና ከሴት ያደረገ ቢሆንም አደምን ያለ አባት ያለ እናት፤ ሐዋን ያለ እናት፤ ዒሳን ደግሞ ያለ አባት መፍጠሩን፤
13. ነብያት በአንድ መንገድ የሚጓዙ በአንድ እምነት የሚያምኑ በአንድ መመሪያ የሚመሩ ወደ አላህ ብቻ የሚጠሩ መሆናቸውን እንማራለን።

وَحَرَٰمٌ عَلَىٰ قَرۡيَةٍ أَهۡلَكۡنَٰهَآ أَنَّهُمۡ لَا يَرۡجِعُونَ ﴿٩٥﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا فُتِحَتۡ يَأۡجُوجُ وَمَأۡجُوجُ وَهُم مِّن كُلِّ حَدَبٖ يَنسِلُونَ ﴿٩٦﴾ وَٱقۡتَرَبَ ٱلۡوَعۡدُ ٱلۡحَقُّ فَإِذَا هِيَ شَٰخِصَةٌ أَبۡصَٰرُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يَٰوَيۡلَنَا قَدۡ كُنَّا فِي غَفۡلَةٖ مِّنۡ هَٰذَا بَلۡ كُنَّا ظَٰلِمِينَ ﴿٩٧﴾

**95-97.** ባጠፉናትም ከተማ ላይ እነርሱ ወደ እኛ የማይመለሱ መሆናቸው እብለት ነው። (ጭራሽ የማይታሰብነው) (ይመለሳሉና)። የእጁጅና መእጁጅም እነርሱ ከየተረተሩ የሚንደረደሩ ሲሆኑ ግድባቸው በተከፈተ ጊዜ፤ እውነተኛውም ቀጠሮ በቀረበ ጊዜ ያንን ጊዜ እነሆ የነዚያ የካዱት ሰዎች ዓይኖች ይፈጥጣሉ። ዋ፣ ጥፍታቸው ከዚያ ቀን በእርግጥ በዝንጋቴ ላይ ነበርን። በእውነትም በዳዮች ነበርን ይላሉ።

إِنَّكُمۡ وَمَا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ حَصَبُ جَهَنَّمَ أَنتُمۡ لَهَا وَٰرِدُونَ ﴿٩٨﴾
لَوۡ كَانَ هَٰٓؤُلَآءِ ءَالِهَةً مَّا وَرَدُوهَاۖ وَكُلٌّ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٩٩﴾ لَهُمۡ فِيهَا زَفِيرٌ
وَهُمۡ فِيهَا لَا يَسۡمَعُونَ ﴿١٠٠﴾

**98-100.** (ከሓዲያን ሆይ!) እናንተና ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣዖታት የገሀነም ማገዶዎች ናችሁ። እናንተ ለእርሷ ወራጆች ናችሁ። እነዚህ ጣዖታት አማልክት በነበሩ ኖሮ ገሀነምን አይገቡዋትም ነበር። ግን ሁሉም በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። እነርሱ በእርሷ ውስጥ ይንሰቀሰቃሉ። እነርሱም በውስጧ ምንንም አይሰሙም።

إِنَّ ٱلَّذِينَ سَبَقَتۡ لَهُم مِّنَّا ٱلۡحُسۡنَىٰٓ أُوْلَٰٓئِكَ عَنۡهَا مُبۡعَدُونَ ﴿١٠١﴾
لَا يَسۡمَعُونَ حَسِيسَهَاۖ وَهُمۡ فِي مَا ٱشۡتَهَتۡ أَنفُسُهُمۡ خَٰلِدُونَ ﴿١٠٢﴾
لَا يَحۡزُنُهُمُ ٱلۡفَزَعُ ٱلۡأَكۡبَرُ وَتَتَلَقَّىٰهُمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ هَٰذَا يَوۡمُكُمُ ٱلَّذِي كُنتُمۡ تُوعَدُونَ ﴿١٠٣﴾

**101-103.** እነዚያ ከእኛ መልካምዋ ቃል ለእነርሱ ያለፈችላቸው እነዚያ ከእርሷ የተራቁ ናቸው። ድምጽዋን አይሰሙም። እነርሱም ነፍሶቻቸው በሚሹት ነገር ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። ታላቁ ድንጋጤ አያስተክዛቸውም። መላእክትም ይህ ያ ትቀጠሩት የነበራችሁት ቀናችሁ ነው እያሉ ይቀበሏቸዋል።

ከነብያት ምዕራፍ (101) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዚሁ (98) ቁጥር ላይ ያለ አንቀፅ ሲወርድ ቁረይሾች በጣም ከበዳቸውና ሙሐመድ እኮ ጌቶቻችንን እየሰደበ ነው ሲሉ ኢብኑ ዚብራ መጥቶ ምን ሆናቹሁ ሲላቸው ጌቶቻችንን እየሰደበ እኮ አሉት ምን አለ ሲላቸው እንዲህ እያለ ነዋ አሉት። በዚህ ጊዜ ለእኔ ጥሩልኝ ብሎ ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) አስጠርቶ ይህ ጉዳይ ለእኛ አማልክት ብቻ ነው ወይም ለሁሉም በማለት ጠይቃቸው ለሁሉም ነው ሲሉት በካዕባ ጌታ ይሁንብኝ ዛሬ ተረኛ መለይኮችና ዓሳ ሣሊሆች ናቸው ትል የለ እነሆ በኑሙለይካ መለይኮችን፤ ነሷሮች ዒሣን፤ አይሁድ ዑዘይርን እያመለኩ አይደለም በማለት ሲናገር መኮች በአንድ ጊዜ በደስታ ጮኸው ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

يَوۡمَ نَطۡوِي ٱلسَّمَآءَ كَطَيِّ ٱلسِّجِلِّ لِلۡكُتُبِۚ كَمَا بَدَأۡنَآ أَوَّلَ خَلۡقٖ نُّعِيدُهُۥۚ وَعۡدًا عَلَيۡنَآۚ
إِنَّا كُنَّا فَٰعِلِينَ ﴿١٠٤﴾ وَلَقَدۡ كَتَبۡنَا فِي ٱلزَّبُورِ مِنۢ بَعۡدِ ٱلذِّكۡرِ أَنَّ ٱلۡأَرۡضَ يَرِثُهَا عِبَادِيَ
ٱلصَّٰلِحُونَ ﴿١٠٥﴾ إِنَّ فِي هَٰذَا لَبَلَٰغٗا لِّقَوۡمٍ عَٰبِدِينَ ﴿١٠٦﴾

**104-106.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለመጽሐፎች የሆኑ ገፆች እንደሚጠቀለሉ ሁሉ ሰማይን የምንጠቀልልበትን ቀን (አስታውስ)። የመጀመሪያን ፍጥረት እንደ ጀመርን እንመልሰዋለን። ይህን መፈፀሙ የማይቀር ቀጠሮን ቀጠርን። እኛ የቀጠርነውን ሰሪዎች ነን። ምድርንም መልካሞች ባሮቼ ይወርሷታል ማለትን ከመጽሐፉ (ከተጠበቀው ሰሌዳ) በኋላ በመጽሐፎች በእርግጥ ጽፈናል። በዚህ ቁርኣን ውስጥ ያሉት ህግጋት ለአላህ ተገዢ ህዝቦች ሁሉ በቂ ናቸው አለ።

وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا رَحۡمَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٠٧﴾

**107.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለዓለማት እዝነት አድርገን እንጅ አልላክንህም።

قُلۡ إِنَّمَا يُوحَىٰٓ إِلَيَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمۡ إِلَٰهٞ وَٰحِدٞۖ فَهَلۡ أَنتُم مُّسۡلِمُونَ ﴿١٠٨﴾ فَإِن تَوَلَّوۡاْ فَقُلۡ
ءَاذَنتُكُمۡ عَلَىٰ سَوَآءٖۖ وَإِنۡ أَدۡرِيٓ أَقَرِيبٌ أَم بَعِيدٞ مَّا تُوعَدُونَ ﴿١٠٩﴾ إِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلۡجَهۡرَ مِنَ
ٱلۡقَوۡلِ وَيَعۡلَمُ مَا تَكۡتُمُونَ ﴿١١٠﴾ وَإِنۡ أَدۡرِي لَعَلَّهُۥ فِتۡنَةٞ لَّكُمۡ وَمَتَٰعٌ إِلَىٰ حِينٖ ﴿١١١﴾ قَٰلَ رَبِّ
ٱحۡكُم بِٱلۡحَقِّۗ وَرَبُّنَا ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلۡمُسۡتَعَانُ عَلَىٰ مَا تَصِفُونَ ﴿١١٢﴾

**108-112.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያ ወደ እኔ የሚወርደው መልዕክት አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው ማለት ነው። ታዲያ እናንተ ፍፁም ታዛዦች ናችሁን? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እምቢ ቢሉ በማወቅ በእኩልነት ላይ ሆነን የታዘዝኩትን አሳውቃችኋለሁ። የምትስፈራሩበትም ነገር ቅርብ ወይም ሩቅ መሆኑን አላውቅም በላቸው። እርሱ ከንግግር ጩኸቱን ያውቃል። የምትደብቁትን ሁሉ ያውቃል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱም ቅጣትን ማቆየት ምናልባት ለእናንተ ፈተናና እስከ ጊዜው መጣቀሚያ እንደ ሆነም አላውቅም (በላቸው)። ጌታዬ ሆይ፤ በእውነት ፍረድ። ጌታችንም እጅግ በጣም ሩህሩህን በምትሉት ነገር ላይ መታገዣ ነው አለ።

**ከነብያት ምዕራፍ ከአንቀፅ (93-112) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ያለፉት ህዝቦች መከፋፈላቸውንና ከአንድ ነብይ ተከታዩች እንኳን እርስ በእርስ እስከመገዳደል እንደደረሱ፤
2. መልካም ስራ ዋጋ እንዲኖረው እምነት አስፈላጊ መሆኑን፤
3. መልካም ስራ እምንትም የሚያፈራው በመልካም ስራ መሆኑን፤

4. የመልካም ስራ ክፍያ በዚህኛው ዓለም ሊጀመር ቢችልም ዋናው በሁለተኛው ዓለም እንደሆነ፤
5. የዕጁጅና መዕጁጅ የሚባሉ ዘሮች መውጣታቸው ከትንሳኤ ቀን መድረስ ምልክቶች አንዱ መሆኑን፤
6. ትክክለኛ አምነትና በመልካም ስራ የታነፁ ሰዎች በመቸውም ጊዜ ቢሆን የዚህ ምድር ወራሾች መሆናቸውን፤
7. የነብዩ (ﷺ) መላክ ለህዝቦቻቸው ብቻ ሳይሆን ለሰው ልጆች በጠቅላላ ረህመት መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የነብያት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (22)
# የሐጅ ምዕራፍ
# (ሱረቱ አል ሐጅ)

سُورَةُ الحَجِّ

## የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ (78) ናቸው።
## የሱረቱ አል ሐጅ መግቢያ

ከአስገራሚ ምእራፎች አንዱ ነው ብለው ኢማሙ ቁርጡቢ ካወሷቸው መካከል ሌሊትም ቀንም በመንገድ ላይ እያሉ በአገር ቤት እያሉ በመካም እያሉ በመዲናም እያሉ በሰላምም እያሉም በጦርነት እያሉም የወረደ ነው።

መልዕክቱን ሲጀምር በአላህ በማስፈራራትና ስለ ቂያማ ቀን በማስጠንቀቅ ነው። ያለ እውቀት የሚከራከሩትንም ክፍሎች አንስቶ ሞቶ መነሳት እውነት ለመሆኑ በቂ ማስረጃዎችን ያቀርባል። ስለ አላህ መከራከርንም አንስቶ ውጤቱንም በአጭሩ አስቀምጧል። ስለ ሐጅና ሥርዓቱም በአጭሩ አመልክቶ ለሙስሊሞች ከላያቸው ላይ ጠላትን መከላከል እንደተፈቀደላቸው ያስተምራል። በማስከተልም ነብዩን (ﷺ) ሰዎች በሚያደርሱባቸው ስቃይና አዛ እንዳይበሳጩ ያለፉትን ጊዜዎችና ታሪኮችን በማውሳት ያፅናናል። የአላህን ኃያልነትና ብቸኛ አምላክነት የነብያትን ተልዕኮ በመወሰንና እሱም ማስተማር እንጂ ማስገደድ እንዳልሆነ በግልፅ ያሳያል። በስተመጨረሻም በጣኦት አምላኪዎች እምነት አምላክነት የተሰጣቸው ዝምብን እንኳን መፍጠር የማይችሉ መሆናቸውን ብሎም ዝምቡ አንድ ነገር ቢቀማቸው ንብረታቸውን ማስመለስ የማይችሉ ሞኝ መሆናቸውን በግልፅ ከተነተነላቸው በኋላ ሶላት፣ ዘካ፣ ጂሃድ ማድረግ እንዳለባቸው ለሙስሊሞች ጥሪ ያደርጋል። ከዚያ ይህ መንገድ የነብዩ ኢብራሂም መንገድ ነብዩ (ﷺ) በእናንት ላይ የሚመሰክርባቸሁ እናንተም ባለፉት ህዝቦች ላይ የምትመሰክሩ መሆናችሁን እወቁ በማለት ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمۡۚ إِنَّ زَلۡزَلَةَ ٱلسَّاعَةِ شَيۡءٌ عَظِيمٞ ١ يَوۡمَ تَرَوۡنَهَا تَذۡهَلُ
كُلُّ مُرۡضِعَةٍ عَمَّآ أَرۡضَعَتۡ وَتَضَعُ كُلُّ ذَاتِ حَمۡلٍ حَمۡلَهَا وَتَرَى ٱلنَّاسَ سُكَٰرَىٰ وَمَا هُم
بِسُكَٰرَىٰ وَلَٰكِنَّ عَذَابَ ٱللَّهِ شَدِيدٞ ٢

**1-2.** እናንተ ሰዎች ሆይ! ጌታችሁን ፍሩ። የሰዓቲቱ እንቅጥቃጤ በጣም ከባድ ነገር ነውና። በምታዩዋት ቀን አጥቢ ሁሉ የአጠባችውን ልጅ ትረሳዋለች። እርጉዝ ሴት ሁሉ እርጉዝዋን ትጨነግፋለች። ሰዎቹንም በድንጋጤ ብርታት የሰከሩ መስለው ታያቸዋለህ። እነርሱ ግን ከመጠጥ የሰከሩ ሳይሆን ግን የአላህ ቅጣት ብርቱ ነውና ነው።

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُجَٰدِلُ فِي ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٖ وَيَتَّبِعُ كُلَّ شَيۡطَٰنٖ مَّرِيدٖ ٣
كُتِبَ عَلَيۡهِ أَنَّهُۥ مَن تَوَلَّاهُ فَأَنَّهُۥ يُضِلُّهُۥ وَيَهۡدِيهِ إِلَىٰ عَذَابِ ٱلسَّعِيرِ ٤

**3-4.** ከሰዎች መካከል ያለ ምንም ዕውቀት በአላህ ነገር የሚከራከር ሞገደኛና ሰይጣንንም የሚከተል ሰው አለ። እነሆ የተከተለውን ሰው እርሱ ያጠመዋል። ወደ አቃጣይ እሳት ስቃይም ይመራዋል ማለት በእርሱ ላይ ተጽፏል። (ተወስኖባቸዋል)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِن كُنتُمۡ فِي رَيۡبٖ مِّنَ ٱلۡبَعۡثِ فَإِنَّا خَلَقۡنَٰكُم مِّن تُرَابٖ ثُمَّ مِن نُّطۡفَةٖ ثُمَّ
مِنۡ عَلَقَةٖ ثُمَّ مِن مُّضۡغَةٖ مُّخَلَّقَةٖ وَغَيۡرِ مُخَلَّقَةٖ لِّنُبَيِّنَ لَكُمۡۚ وَنُقِرُّ فِي ٱلۡأَرۡحَامِ مَا نَشَآءُ إِلَىٰٓ
أَجَلٖ مُّسَمّٗى ثُمَّ نُخۡرِجُكُمۡ طِفۡلٗا ثُمَّ لِتَبۡلُغُوٓاْ أَشُدَّكُمۡۖ وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ وَمِنكُم مَّن
يُرَدُّ إِلَىٰٓ أَرۡذَلِ ٱلۡعُمُرِ لِكَيۡلَا يَعۡلَمَ مِنۢ بَعۡدِ عِلۡمٖ شَيۡـٔٗاۚ وَتَرَى ٱلۡأَرۡضَ هَامِدَةٗ فَإِذَآ أَنزَلۡنَا
عَلَيۡهَا ٱلۡمَآءَ ٱهۡتَزَّتۡ وَرَبَتۡ وَأَنۢبَتَتۡ مِن كُلِّ زَوۡجِۭ بَهِيجٖ ٥ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡحَقُّ
وَأَنَّهُۥ يُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰ وَأَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٦ وَأَنَّ ٱلسَّاعَةَ ءَاتِيَةٞ لَّا رَيۡبَ فِيهَا وَأَنَّ
ٱللَّهَ يَبۡعَثُ مَن فِي ٱلۡقُبُورِ ٧

**5-7.** ሰዎች ሆይ! ከሞት በኋላ ከመቀስቀስ በመጠራጠር ጉዳይ እንደ ሆናችሁ የመጀመሪያውን አፈጣጠራችሁን ተመልከቱ፡፡ እኛም ከዐፈር ፈጠርናችሁ፡፡ ከዚያ ከፍትወት ጠብታ፤ ከዚያ ከረጋ ደም ከዚያ ከቁራጭ ስጋ ፍጥረትዋ ሙሉ ከሆነችና ሙሉ ካልሆነች (ችሎታችንን) ለእናንተ ልንገልጽላችሁ ፈጠርናችሁ፡፡ የምንሻውንም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ በማህፀን ውስጥ እናረጋዋለን፡፡ ከዚያ ህፃን* ሆናችሁ እናወጣችኋለን፡፡ ከዚያም ሙሉ ጥንካሪያችሁን ትደርሱ ዘንድ (እናሳድጋችኋለን)፡፡ ከናንተም መካከል በወጣትነቱ የሚሞት ሰው አለ፡፡ ከናንተም መካከል ከዕውቀት በኋላ ምንንም እንዳያውቅ ወደ ጃጀ ዕድሜ የሚመለስ ሰው አለ፡፡ ምድርንም ደረቅ ሆና ታያታለህ፡፡ በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ ትላወሳለች \ትነቃነቃለች\፡፡ ትነፋለችም፡፡ ውበት ካለው የእፅዋት አይነት ሁሉ ታበቅላለችም፡፡ ይህ ሁሉ አላህ መኖሩ የተረጋገጠ፤ እርሱም ሙታንን ህያው የሚያደርግ፤ እርሱ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ የሰዓቲቱም መከሰት ፈጽሞ ጥርጣሬ የሌለበት በመሆኑና አላህ በመቃብሮች ውስጥ ያለን ሁሉ የሚቀሰቅስ በመሆኑ ነው፡፡

*✶ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እውነተኛውና ታማኙ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) «በእርግጥ የእያንዳንዳችን መሰረተ አካል በእናታችን ማህፀን ውስጥ ለአርባ ቀን በዘር መልክ ይሰበሰባል» ብለዋል፡፡ በተመሳሳይ ቀናትም የረጋ ደም ይሆናል፤ ቀጥሎም ለተመሳሳይ ቀናትም የታኘከ የሚመስል ስጋ ይሆናል፡፡ ከዚያ በኋላ ወደርሱ መልአክ ይላክና አራት ነገሮችን እንዲፈፅም ይታዘዛል፡፡ የዕለት ጉርሱን፤ ዕድሜውን፤ ሥራውንና የተረገመ ወይም የተባረከ መሆኑን ይፅፋል፡፡ ከዚያም ሩህ ይዘራበታል፡፡ በእርግጥ አንድ ሰው የጀሀነም ሰዎችን ተግባር በእርሱና በእሳት መካከል አንድ ክንድ ርቀት እስኪቀር ድረስ ይፈፅማል፡፡ ከዚያም የተፃፈለትን ነገር ይቀድምና የጀነት ሰዎችን ተግባራት ፈፅሞ ጀነት ይገባል፡፡ በእርግጥ አንድ ሰው የጀነት ሰዎችን ተግባራት በጀነትና በርሱ መካከል አንድ ክንድ ርቀት እስኪቀር ድረስ ይፈፅማል፡፡ ከዚያም የተፃፈለትን ነገር ይቀድምና ወደ እሳት ይገባል»*

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُجَٰدِلُ فِي ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٖ وَلَا هُدٗى وَلَا كِتَٰبٖ مُّنِيرٖ ﴿٨﴾
ثَانِيَ عِطۡفِهِۦ لِيُضِلَّ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِۖ لَهُۥ فِي ٱلدُّنۡيَا خِزۡيٞۖ وَنُذِيقُهُۥ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ عَذَابَ
ٱلۡحَرِيقِ ﴿٩﴾ ذَٰلِكَ بِمَا قَدَّمَتۡ يَدَاكَ وَأَنَّ ٱللَّهَ لَيۡسَ بِظَلَّٰمٖ لِّلۡعَبِيدِ ﴿١٠﴾

**8-10.** ከሰዎች መካከል ያለ ምንም ዕውቀት ያለ አንዳች ማስረጃም ያለ አብራሪ መጽሐፍ ጎኑን ያጠፈ ሆኖ ከአላህ መንገድ ሊያሳስት በአላህ ነገር የሚከራከር ሰው አለ፡፡ በቅርቢቱ ዓለም ለርሱ ውርደት አለው፡፡ በትንሳኤ ቀንም አቃጣይን (የእሳት) ቅጣት እናቀምሰዋለን፡፡ ይህ እጆችህ ባስቀደሙት ኃጢአትና አላህም ለባሮቹ ፈጽሞ በዳይ ባለመሆኑ ነው ይባላል፡፡

ከሐጅ ምዕራፍ (8) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- «8 ኛው ልክ እንደ 3 ኛው አንቀፅ ነው» የሚሉ ሰዎች እንዳሉ ሁሉ «በአኽነስ ኢብኑ ሽሪቅ» ምክንያት ነው የሚሉም አሉ፡፡ ሁሉም ተመሳሳይ ባህሪ ያላቸው በመሆናቸው ነው ይህም ሊሆን የቻለው፡፡

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَعۡبُدُ ٱللَّهَ عَلَىٰ حَرۡفٖۖ فَإِنۡ أَصَابَهُۥ خَيۡرٌ ٱطۡمَأَنَّ بِهِۦۖ وَإِنۡ أَصَابَتۡهُ فِتۡنَةٌ
ٱنقَلَبَ عَلَىٰ وَجۡهِهِۦ خَسِرَ ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةَۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡخُسۡرَانُ ٱلۡمُبِينُ ١١ يَدۡعُواْ مِن دُونِ
ٱللَّهِ مَا لَا يَضُرُّهُۥ وَمَا لَا يَنفَعُهُۥۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلضَّلَٰلُ ٱلۡبَعِيدُ ١٢ يَدۡعُواْ لَمَن ضَرُّهُۥٓ أَقۡرَبُ مِن
نَّفۡعِهِۦۚ لَبِئۡسَ ٱلۡمَوۡلَىٰ وَلَبِئۡسَ ٱلۡعَشِيرُ ١٣

**11-13.** ከሰዎች መካከል በሃይማኖት ጫፍ ላይ ሆኖ አላህን የሚገዛ ሰው አለ። እናም መልካም ነገር ካገኘው በእምነቱ ላይ ይረጋል። መከራ ካገኘው ግን በፊቱ ላይ ይገለበጣል (ይከዳል)። ይህ አይነቱ ሰው የቅርቢቱን ዓለምም ሆነ የመጨረሻይቱን ዓለም ከሰረ። ይህ ግልጽ ኪሳራ ማለት ነው። ከአላህ ሌላ የማይጎዳውንና የማይጠቅመውን ይገዛል። ይህ እርሱ ከእውነት የራቀ ስህተት ነው። ያንን ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ወደ እሱ የሚቀርብን ይገዛል። ረዳቱ ምንኛ ከፋ! ወዳጁም ምንኛ ከፋ!

إِنَّ ٱللَّهَ يُدۡخِلُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۚ
إِنَّ ٱللَّهَ يَفۡعَلُ مَا يُرِيدُ ١٤

**14.** አላህ እነዚያን በትክክል ያመኑትንና መልካም ስራዎችን የሰሩትን ሰዎች በስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያስገባቸዋል። አላህ የሚሻውን ነገር በእርግጥ ይሰራልና።

مَن كَانَ يَظُنُّ أَن لَّن يَنصُرَهُ ٱللَّهُ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ فَلۡيَمۡدُدۡ بِسَبَبٍ إِلَى ٱلسَّمَآءِ
ثُمَّ لۡيَقۡطَعۡ فَلۡيَنظُرۡ هَلۡ يُذۡهِبَنَّ كَيۡدُهُۥ مَا يَغِيظُ ١٥ وَكَذَٰلِكَ أَنزَلۡنَٰهُ
ءَايَٰتِۭ بَيِّنَٰتٖ وَأَنَّ ٱللَّهَ يَهۡدِي مَن يُرِيدُ ١٦

**15-16.** አላህ (መልዕክተኛውን) ሙሐመድን በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም አይረዳውም ብሎ የሚያስብ ሰው ካለ ገመድን ወደ ሰማይ ይዘርጋና ከዚያ (ትንፋሹ እስኪቆረጥ) ይታነቅ። ይህ ተግባሩ ያን ተንኮሉ የሚያስቆጨውን ነገር ያስወግደለት እንደሆነም ይመልከት። ልክ እንደዚሁ (ቁርኣንን) የተብራሩ አንቀፆች አድርገን አወረድነው። አላህ የሚሻውን ሰው ሁሉ ይመራልና።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَٱلَّذِينَ هَادُواْ وَٱلصَّٰبِـِٔينَ وَٱلنَّصَٰرَىٰ وَٱلْمَجُوسَ وَٱلَّذِينَ أَشْرَكُوٓاْ
إِنَّ ٱللَّهَ يَفْصِلُ بَيْنَهُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ شَهِيدٌ ﴿١٧﴾

**17.** እነዚያ በአላህ ያመኑ እነዚያ አይሁዳውያን፤ እነዚያ ምንም እምነት የሌላቸው ሳቢያኖች፤ ክርስቲያኖችም፤ መጁሶች እና እነዚያም (ጣዖታትን በአላህ) ያጋሩ ሁሉ አላህ በትንሳኤ ቀን በመካከላቸው በፍርድ ይለያል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ በእርግጥ ዐዋቂ ነውና።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَسْجُدُ لَهُۥ مَن فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِى ٱلْأَرْضِ وَٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ وَٱلنُّجُومُ
وَٱلْجِبَالُ وَٱلشَّجَرُ وَٱلدَّوَآبُّ وَكَثِيرٌ مِّنَ ٱلنَّاسِۖ وَكَثِيرٌ حَقَّ عَلَيْهِ ٱلْعَذَابُۗ وَمَن يُهِنِ ٱللَّهُ
فَمَا لَهُۥ مِن مُّكْرِمٍۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَفْعَلُ مَا يَشَآءُ ۩ ﴿١٨﴾

**18.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ፀሐይና፤ ጨረቃም፤ ከዋክብትም፤ ተራሮችም፤ ዛፎችም፤ ተንቀሳቃሾችም ፍጡራንና ከሰዎች ብዙዎችም ለእርሱ የሚሰግዱለት መሆኑን አታውቅምን?* ከሰዎች ብዙውም በእርሱ ላይ የአላህ ቅጣት ተረጋገጠበት። አላህ የሚያዋርደው ሰው ለእርሱ ምንም አክባሪ የለውም። አላህ የሻውን ይሰራልና።

* ከዚህ አባባል የምንማረው ቁም ነገር መስገድ በሰዎች በጋኔንና በመላይኮች ብቻ የተወሰነ አለመሆኑን ነው። «ሰባቱ ሰማያትና ምድርም በውስጣቸው ያለው ሁሉ ለእርሱ ያጠራሉ። ከነገሩም ሁሉ ከማመስገን ጋር የሚጠራው እንጂ.» (17/44) «ለሱለይማንም (ትክክለኛይቱን ፍርድ) አሳወቅን፤ ለሁሉም ጥበብና እውቀትን ሰጠን ተራራዎችንም ከዳውድ ጋር የሚያወድሱ ....» (21/79) እና «ተራራዎችን ከቀትር በኋላና በረፋድም ከርሱ ...» (38/18)

ከሐጅ ምዕራፍ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- መዲና የነበሩ ዘላኖች ሰልመው ይመጡና ኑሯቸው ከተመቻቸና ሀብታቸው ከበረከተ ሚስቶቻቸው ወንድ ከወለዱና ጤና ካገኙ «ኢስላም ገጥሞኛል» በማለት ይደሰታሉ። ይህ ካልሆነ ግን ሁኔታው እንዳልገጠማቸውና ኢስላም እንደማይሆናቸው ያምኑ ሥለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

۞هَٰذَانِ خَصْمَانِ ٱخْتَصَمُواْ فِى رَبِّهِمْۖ فَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ قُطِّعَتْ لَهُمْ ثِيَابٌ مِّن نَّارٍ
يُصَبُّ مِن فَوْقِ رُءُوسِهِمُ ٱلْحَمِيمُ ﴿١٩﴾ يُصْهَرُ بِهِۦ مَا فِى بُطُونِهِمْ وَٱلْجُلُودُ ﴿٢٠﴾
وَلَهُم مَّقَٰمِعُ مِنْ حَدِيدٍ ﴿٢١﴾ كُلَّمَآ أَرَادُوٓاْ أَن يَخْرُجُواْ مِنْهَا مِنْ غَمٍّ أُعِيدُواْ فِيهَا
وَذُوقُواْ عَذَابَ ٱلْحَرِيقِ ﴿٢٢﴾

**19-22.** እነዚህ በጌታቸው ጉዳይ የተከራከሩ ሁለት ባለጋራዎች ናቸው። እነዚያ በአላህ የካዱት የእሳት ልብሶች ተለክተውላቸዋል፤ ከራሶቻቸው ላይ የፈላ ውሃ ይምቧቧባቸዋል። በሆዶቻቸው ውስጥ ያለውና ቆዳዎቻቸው በርሱ ይቀልጣሉ። ለነሱም (መቅጫ) ከብረት የሆኑ መዶሻዎች አሉ። ከጭንቀት ብርታት የተነሳ ከርሷ ለመውጣት በፈለጉ ቁጥር በእርሷ ውስጥ እንዲመለሱ ይደረጋሉ። በጣም የሚያቃጥለውን ቅጣት ቅመሱ ይባላሉ።

ከሐጅ ምዕራፍ (19) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከሙስሊሙ ወገን ሀምዛ፤ ዑበይዳህና ዓልይ ከከሓዲያን ወገን ዑትባህ፤ ሸይበህ እና ወሊድ ቢን ዑትባህ ሆነው ባካሄዱት ፍልሚያም ነው ይህ አንቀፅ የወረደው የሚሉ ብዙዎች ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በአይሁዶችና በሙስሊሞች መካከል በነበረው ክርክር ነው ይላሉ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱللَّهَ يُدۡخِلُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ يُحَلَّوۡنَ فِيهَا مِنۡ أَسَاوِرَ مِن ذَهَبٖ وَلُؤۡلُؤٗاۖ وَلِبَاسُهُمۡ فِيهَا حَرِيرٞ ٢٣ وَهُدُوٓاْ إِلَى ٱلطَّيِّبِ مِنَ ٱلۡقَوۡلِ وَهُدُوٓاْ إِلَىٰ صِرَٰطِ ٱلۡحَمِيدِ ٢٤

**23-24.** አላህ እነዚያን በትክክል ያመኑትንና መልካም ስራዎችን የሰሩትን ሰዎች በስሮቻቸው ጅረት ወንዞች በሚፈሱባቸው ገነቶች ያስገባቸዋል። በእርሷ ውስጥ የወርቅ አንባሮችና ሉልን ይሸለማሉ። በእርሷ ውስጥ ልብሶቻቸውም ከሐር የተሰሩ ናቸው። ከእነርሱ ቡድኖች ወደ መልካም ንግግርና ወደ ምስጉን መንገድ ተመሩ።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَيَصُدُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ ٱلَّذِي جَعَلۡنَٰهُ لِلنَّاسِ سَوَآءً ٱلۡعَٰكِفُ فِيهِ وَٱلۡبَادِۚ وَمَن يُرِدۡ فِيهِ بِإِلۡحَادِۭ بِظُلۡمٖ نُّذِقۡهُ مِنۡ عَذَابٍ أَلِيمٖ ٢٥

**25.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎችን ከአላህ መንገድና ከዚያ ለሰዎች በውስጡ ነዋሪ ለሆኑትም ሆነ ከሩቅ ለሚመጡት (ሰዎች) እኩል ካደረግነው ከተከበረው መስጊድ የሚከለክሉ ሁሉ በእርሱም ውስጥ ከትክክለኛ መንገድ በመዘንበል ራሱን በዳይ ሆኖ (ማንኛውንም ነገር) የሚያስብ ሰው ከአሳማሚ ቅጣት እናቀምሰዋለን።

ከሐጅ ምዕራፍ (25) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አብደላህ ኢብኑ ኡነይስ የተባለ ሰው ከሁለት ወንዶች ጋር መንገድ እየሄዱ ሳለ በዘር መፎካከር ጀመሩ። በክርክሩም ወቅት አብደላ ኢብኑ ኡነይስ ስለተናደደ አንዱን ገድሎ ኢስላምንም ጥሎ ወደ መካ በመሸሹ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

**ከሐጅ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-25) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ ይህን በተመለከተ ሰፊ መግለጫ መስጠት፤
2. ሀቅን ለማረጋገጥ መስራት ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. ያለ እውቀት ስለ አላህ ማንነትም ሆነ ባህሪያት መናገር ክልክል ስለመሆኑ፤
4. ሰይጣንን መከተልና ወዳጅ አድርጎ መያዝ ለጀሀነም እንደሚያበቃ፤
5. ምስጉን መንገድ ምን ማለት እንደሆነ ማስተማር፤
6. የሰው ልጅ እድገትን በተመለከተ፤
7. በአይን በሚታይና በእጅ የሚዳሰስን ነገር በማውሳት የሩቅን ነገር ማስተማር፤
8. ጥሩ ንግግር ማለት ምን እንደሆነ ማስተማር፤
9. ኩራትና ትዕቢተኛነትን ማውገዝ፤
10. እየተጠራጠሩ የሚሰሩት ዒባዳ ፋይዳ ቢስ መሆኑን፤
11. ከኢስላም ሌላ ያሉ እምነቶች በሙሉ የሰይጣን ተልዕኮዎች ስለመሆናቸው፤
12. አላህ ዲኑን እንደሚረዳ፤
13. አላህ የፈለገውን ማድረግ እንደሚችል፤
14. ከሃዲና አማኝ መቼውንም እንደማይስማሙ፤
15. የከሃዲም ሆነ የአማኝ ምንዳው ምን እንደሚመስል፤
16. ክህደትን ማውገዝ፤
17. መካ ምእመናን ሁሉ መሆንዋን፤
18. የሀረም ክብር ከፍተኛ ስለመሆኑ እንማራለን።

وَإِذْ بَوَّأْنَا لِإِبْرَٰهِيمَ مَكَانَ ٱلْبَيْتِ أَن لَّا تُشْرِكْ بِى شَيْـًٔا وَطَهِّرْ بَيْتِىَ لِلطَّآئِفِينَ
وَٱلْقَآئِمِينَ وَٱلرُّكَّعِ ٱلسُّجُودِ ﴿٢٦﴾ وَأَذِّن فِى ٱلنَّاسِ بِٱلْحَجِّ يَأْتُوكَ رِجَالًا وَعَلَىٰ كُلِّ
ضَامِرٍ يَأْتِينَ مِن كُلِّ فَجٍّ عَمِيقٍ ﴿٢٧﴾ لِّيَشْهَدُوا۟ مَنَٰفِعَ لَهُمْ وَيَذْكُرُوا۟ ٱسْمَ ٱللَّهِ فِىٓ أَيَّامٍ
مَّعْلُومَٰتٍ عَلَىٰ مَا رَزَقَهُم مِّنۢ بَهِيمَةِ ٱلْأَنْعَٰمِ ۖ فَكُلُوا۟ مِنْهَا وَأَطْعِمُوا۟ ٱلْبَآئِسَ ٱلْفَقِيرَ ﴿٢٨﴾
ثُمَّ لْيَقْضُوا۟ تَفَثَهُمْ وَلْيُوفُوا۟ نُذُورَهُمْ وَلْيَطَّوَّفُوا۟ بِٱلْبَيْتِ ٱلْعَتِيقِ ﴿٢٩﴾ ذَٰلِكَ ۖ وَمَن يُعَظِّمْ
حُرُمَٰتِ ٱللَّهِ فَهُوَ خَيْرٌ لَّهُۥ عِندَ رَبِّهِۦ ۗ وَأُحِلَّتْ لَكُمُ ٱلْأَنْعَٰمُ إِلَّا مَا يُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ ۖ
فَٱجْتَنِبُوا۟ ٱلرِّجْسَ مِنَ ٱلْأَوْثَٰنِ وَٱجْتَنِبُوا۟ قَوْلَ ٱلزُّورِ ﴿٣٠﴾ حُنَفَآءَ لِلَّهِ غَيْرَ مُشْرِكِينَ
بِهِۦ ۚ وَمَن يُشْرِكْ بِٱللَّهِ فَكَأَنَّمَا خَرَّ مِنَ ٱلسَّمَآءِ فَتَخْطَفُهُ ٱلطَّيْرُ أَوْ تَهْوِى بِهِ ٱلرِّيحُ فِى
مَكَانٍ سَحِيقٍ ﴿٣١﴾ ذَٰلِكَ ۖ وَمَن يُعَظِّمْ شَعَٰٓئِرَ ٱللَّهِ فَإِنَّهَا مِن تَقْوَى ٱلْقُلُوبِ ﴿٣٢﴾ لَكُمْ
فِيهَا مَنَٰفِعُ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى ثُمَّ مَحِلُّهَآ إِلَى ٱلْبَيْتِ ٱلْعَتِيقِ ﴿٣٣﴾

**26-33.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለኢብራሂም የቤቱን የከዕባን ስፍራ መመለሻ ባደረግንለት ጊዜ በኔ ምንንም አታጋራ። ቤቴንም ለሚዘይሩትና ለሚቆሙበት (ለስግደት) ለሚያጎነብሱትና በግንባራቸውም ለሚደፉት (ሩኩዕና ሱጁድ ለሚያደርጉት) ንፁህ አድርግላቸው ባልነው ጊዜ (የሆነውን ለህዝቦችህ አስታውስ)። ኢብራሂም ሆይ፣ በሰዎች መካከል የሐጅን ትእዛዝ አሰማ። እግረኞችና ከየሩቅ መንገድ* በሚመጡ ከሲታ ግመሎች ሁሉ ላይ እንኳን ሆነውም ይመጡልሃልና። ለእነርሱ የሆነ ጥቅሞችን ያገኙ ዘንድና በእነዚያ በታወቁ ቀኖችም ውስጥ ከለማዳ እንስሳዎች በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ያወሱ ዘንድ ይመጡልሃል። ከእርሷም ብሉ። ችግረኛንም አብሉ። ከዚያ (እንደ ጠጉርና ጥፍር ያሉትን) ትርፍ አካላቸውንና እድፋቸውን ያስወግዱ። ስለቶቻቸውንም በትክክል ይሙሉ። በጥንታዊውም ቤት በካዕባ ዙሪያ ይዙሩ አልን። የሐጅ ሥርአት ይህ ነው። የአላህን ህግጋት የሚያከብር ሰው ሁሉ እርሱ እጌታው ዘንድ ለእርሱ በጣም የተሻለ መልካም ነው። የቤት እንስሳትም በእናንተ ላይ እርም መሆኑ ከሚነበብላችሁ በስተቀር ለእናንተ ተፈቅዳላችኋለች። ከጣዖታትም ርክሰት ተጠንቀቁ። ሐሰትንም ቃል ራቁ። ለአላህ በእርሱ የማታጋሩ ሆናችሁ ወደ ቀጥተኞች መንገድ የተዘነበላችሁ (ታዛዦች) ሁኑ። በአላህ የሚያጋራ ሰው ሁሉ ከሰማይ እንደ ወደቀና በራሪ እንደምትነጥቀው ወይም ንፋስ በሩቅ ስፍራ እንደምትጥለው ነው። ነገሩ ይህ ነው። የአላህን ሃይማኖታዊ ምልክቶች የሚያከብር ሰው ሁሉ ድርጊቱ አላህን ከሚፈሩ ልቦች የሚፈፀም ጥንቃቄ ነው። ለእናንተ በእርሷ እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ጥቅሞች አሏችሁ። ከዚያ የማረጃ (የኡሁዱህያ) ስፍራ እጥንታዊው ቤት አጠገብ ነው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ይህን ቤት ካዕባ ሐጅ ያደረገ ሐጅ በሚያደርግበት ጊዜ ከባለቤቱ ጋር ያልተገናኘና መጥፎ ነገር ያልተናገረ ልክ እንደ ተወለደ ህፃን ወንጀል እንደሌለበት ሆኖ ይመለሳል»

وَلِكُلِّ أُمَّةٍ جَعَلْنَا مَنسَكًا لِّيَذْكُرُوا۟ ٱسْمَ ٱللَّهِ عَلَىٰ مَا رَزَقَهُم مِّنۢ بَهِيمَةِ ٱلْأَنْعَٰمِ ۗ فَإِلَٰهُكُمْ
إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَلَهُۥٓ أَسْلِمُوا۟ ۗ وَبَشِّرِ ٱلْمُخْبِتِينَ ﴿٣٤﴾ ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَجِلَتْ قُلُوبُهُمْ
وَٱلصَّٰبِرِينَ عَلَىٰ مَآ أَصَابَهُمْ وَٱلْمُقِيمِى ٱلصَّلَوٰةِ وَمِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿٣٥﴾

**34-35.** ከቤት እንስሳት በሰጣቸው ሲሳይ ላይ የአላህን ስም ብቻ ያወሱ ዘንድ ለህዝቦች ሁሉ (ወደ አላህ) መስዋዕት ማቅረብን ሀይማኖታዊ ሥርአቶችን ደነገግን። አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው። እርሱንም ብቻ ታዘዙ።

ለአላህ ተዋራጆችንም በመልካም ነገር አብስራቸው። እነዚያን አላህ በተወሳ ጊዜ ልቦቻቸው የሚጨነቁትን (የሚፈሩትን) በደረሰባቸውም መከራ ላይ ታጋሾችን፤ ሰላትንም አስተካክለው ሰጋጆችን ከሰጠናቸውም ሲሳይ የሚለግሱትን በጀነት አብስር።

وَٱلۡبُدۡنَ جَعَلۡنَٰهَا لَكُم مِّن شَعَٰٓئِرِ ٱللَّهِ لَكُمۡ فِيهَا خَيۡرٞۖ فَٱذۡكُرُواْ ٱسۡمَ ٱللَّهِ عَلَيۡهَا صَوَآفَّۖ فَإِذَا وَجَبَتۡ جُنُوبُهَا فَكُلُواْ مِنۡهَا وَأَطۡعِمُواْ ٱلۡقَانِعَ وَٱلۡمُعۡتَرَّۚ كَذَٰلِكَ سَخَّرۡنَٰهَا لَكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ٣٦ لَن يَنَالَ ٱللَّهَ لُحُومُهَا وَلَا دِمَآؤُهَا وَلَٰكِن يَنَالُهُ ٱلتَّقۡوَىٰ مِنكُمۡۚ كَذَٰلِكَ سَخَّرَهَا لَكُمۡ لِتُكَبِّرُواْ ٱللَّهَ عَلَىٰ مَا هَدَىٰكُمۡۗ وَبَشِّرِ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ٣٧ ۞ إِنَّ ٱللَّهَ يُدَٰفِعُ عَنِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ خَوَّانٖ كَفُورٍ ٣٨

**36-38.** ግመሎችንም ለእናንተ ከአላህ ሃይማኖት ምልክቶች አደረግናቸው፤ በነርሱ ለእናንተ ብዙ መልካም ጥቅሞች አሏችሁ፤ በእርሷም ላይ ስታርዷት በሦስት እግሮችዋ ቆማ የተሰለፈች ሆና የአላህን ስም አውሱ። ጎኖቻቸውም በወደቁ ጊዜ ከእርሷ ብሉ። በግልፅ ለማኙንም ለልመና የሚያገዳድምንም አብሉ። ልክ እንደዚሁ ታመሰግኑ ዘንድ ለእናንተ ገራናት። አላህን ስጋዎቿም ሆኑ ደሞቿም ፈጽሞ አይደርሰውም። ለእናንተ ግን ከናንተ የሆነው ፍራቻ ብቻ ይደርሰዋል። እንደዚሁ አላህን በመራችሁ ላይ ልታከብሩት ለእናንተ ገራት በጎ ሰሪዎችንም አብስር። አላህ ከእነዚያ በሱ ካመኑት ሰዎች ላይ የከሓዲያንን ተንኮል ይከላከልላቸዋል። አላህ ከዓተኛንና ውለታ ቢስን ሁሉ አይወድም።

ከሐጅ ምዕራፍ (37) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በጃሂሊያ ዘመን ሰዎች በግመል ሥጋና ደም ካዕባንን ይለቀልቁት ስለነበር ሶሃቦች ይህን ነገር መፈፀም ተገቢ ከሆነ እኛ እንቀድማለን በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)።

أُذِنَ لِلَّذِينَ يُقَٰتَلُونَ بِأَنَّهُمۡ ظُلِمُواْۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ نَصۡرِهِمۡ لَقَدِيرٌ ٣٩ ٱلَّذِينَ أُخۡرِجُواْ مِن دِيَٰرِهِم بِغَيۡرِ حَقٍّ إِلَّآ أَن يَقُولُواْ رَبُّنَا ٱللَّهُۗ وَلَوۡلَا دَفۡعُ ٱللَّهِ ٱلنَّاسَ بَعۡضَهُم بِبَعۡضٖ لَّهُدِّمَتۡ صَوَٰمِعُ وَبِيَعٞ وَصَلَوَٰتٞ وَمَسَٰجِدُ يُذۡكَرُ فِيهَا ٱسۡمُ ٱللَّهِ كَثِيرٗاۗ وَلَيَنصُرَنَّ ٱللَّهُ مَن يَنصُرُهُۥٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَقَوِيٌّ عَزِيزٌ ٤٠ ٱلَّذِينَ إِن مَّكَّنَّٰهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ أَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتَوُاْ ٱلزَّكَوٰةَ وَأَمَرُواْ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَنَهَوۡاْ عَنِ ٱلۡمُنكَرِۗ وَلِلَّهِ عَٰقِبَةُ ٱلۡأُمُورِ ٤١

**39-41.** ለእነዚያ በከሓዲያን ለሚገደሉት አማኞች የተበደሉ በመሆናቸው መጋደል ተፈቀደላቸው። አላህ እነርሱን በመርዳት ላይ በእርግጥ ቻይ ነው። ለእነዚያ ጌታችን አላህ ነው ከማለታቸው በስተቀር ያለ አግባብ ከየቀያቸው የተባረሩ ለሆኑት ከራሳቸው ላይ መከላከል ተፈቀደ። አላህ ሰዎችን ከፊላቸውን በከፊሉ መገፍተሩ ባልነበረ ኖሮ ገዳማት ቤተክርስቲያኖችም ምኩራቦችና በውስጣቸው የአላህ ስም በብዛት የሚወሳባቸው መስጊዶች በተፈረሱ ነበር። አላህ ሃይማኖቱን የሚረዳውን ሰው ሁሉ በእርግጥ ይረዳዋል። አላህ ብርቱና አሸናፊ ነውና። እነርሱ ማለት እነዚያ በምድር ላይ ብናስመቻቻው (የበላይነትን ሰጥተን ባጎናፀፍናቸው ኖሮ) ሶላትን እንደሚገባ የሚያስተካክሉ፤* ዘካንም የሚሰጡ፤ በደግ ነገርም የሚያዝዙ፤ ከመጥፎ ነገር የሚከለከሉ ናቸው። የነገሮች ሁሉ መጨረሻ ወደ አላህ ብቻ ነው።

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «በመናፍቃን ላይ ከባድ የሆኑ ሶላቶች የፈጅርና የዒሻ ሶላቶች ናቸው። እነዚህ መናፍቃን በነዚህ የሶላት ወቅቶች መካከል ያለውን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እየተንተቱም ቢሆን በመስጂድ ይገኙ ነበር።»

ከሐጅ ምዕራፍ (39) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሀ ነብዩ (ﷺ) ከመካ ሲወጡ አቡበክር ነብያቸውን አስወጡ ወላሂ ይጠፋሉ ስላሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)። ሙስሊሞች በመካ ሲኖሩ ተደብድበው ቆስለው እየመጡ ለነብዩ (ﷺ) ሲናገሩ «ታገሱ ጦርነት አልተፈቀደልኝም» ይሏቸው ሥለነበር መዲና እንደሄዱ ይህ አንቀፅ ወረደ። እና ራሳቸውን መከላከል እንደሚችሉ አሳወቀ። ያሉም አሉ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከሐጅ ምዕራፍ ከአንቀፅ (26-41) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሁሉም ነገር መታደስ አስፈላጊው ሆኖ በተገኘ ጊዜ መታደሱ ግዴታ መሆኑን፤
2. ስለ ሐጅ የሚያስተምሩ ቢሮዎችን መክፈት አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
3. ወደ ሐጅ የሄደ ሰው መነገድ እንደሚችል፤
4. አላህን ማመስገንና ማወደሱ ተገቢ ስለመሆኑ፤
5. የሐጅ ሰዎች ከሚያመጧቸው ስጦታዎች መመገብ እንደሚቻል፤
6. ጀምረተል አቀባ የሚባለውን የጠጠር መወርወሪያ ቦታ ከወረወሩ በኋላ ፀጉሩን መላጨት ወይም ማሳጠር ግዴታ መሆኑ፤
7. በሸሪዓ የተፈቀዱ ስለቶችን መሙላት ግዴታ ስለመሆኑ፤
8. ጠዋፈል ኢፋዳ (ግዴታው ጠዋፍ) መቼ መደረግ እንዳለበት መግለፅ፤
9. ቁርባን ማረድ በየትኛውም እምነቶች ላይ የተደነገገ እንደነበረ፤
10. ፈሪሀውንያኖች ምን እንደሆኑ ማሳወቅ፤
11. እንስሳቶች ሲታረዱ የአላህን ስም ማውሳት ግዴታ ስለመሆኑ፤
12. ግመሎች እንዴት እንደሚታረዱ ማስተማር፤
13. በሐጅ ከሚታረዱ እንስሳቶች መመገብና ድሆችን ማብላት ግዴታ ስለመሆኑ፤
14. ለፀጋዎች ሁሉ አላህን ማመስገን፤

15. የሐጅ ፀሎት በሚደረግ ጊዜ አላሁ አክበር ማለቱ ተገቢ ስለመሆኑ፤
16. አላህ በእምነታቸው እውነተኛ ለሆኑ ሰዎች እንደሚከላከልላቸው ቃል መግባቱን፤
17. ከሓዲያንን አላህ እንደሚጠላቸው፤
18. የአላህን ቃል ለማሞገስ እስከ ጦርነት፤ ትግል ማድረግ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
19. አላህ ለባሮቹ ምድርን ያስወረሰበት ምክንያት ሶላትን መስገድ፤ ዘካን መስጠት፤ በመልካም ማዘዝና ከመጥፎ መከልከል መሆኑን፤

وَإِن يُكَذِّبُوكَ فَقَدْ كَذَّبَتْ قَبْلَهُمْ قَوْمُ نُوحٍ وَعَادٌ وَثَمُودُ ﴿٤٢﴾ وَقَوْمُ إِبْرَٰهِيمَ وَقَوْمُ لُوطٍ ﴿٤٣﴾
وَأَصْحَـٰبُ مَدْيَنَ ۖ وَكُذِّبَ مُوسَىٰ ۖ فَأَمْلَيْتُ لِلْكَـٰفِرِينَ ثُمَّ أَخَذْتُهُمْ ۖ فَكَيْفَ كَانَ نَكِيرِ ﴿٤٤﴾

**42-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)) ቢያስተባብሉህ ከእነርሱ በፊት የኑሕ ህዝቦች ዓድና ሰሙድ በእርግጥ አስተባብለዋል። የኢብራሂምም ህዝቦች የሉጥም ህዝቦች እንደዚሁ አስተባብለዋል፤ የመድየንም ሰዎች እንዲሁ አስተባብለዋል። ሙሳም ተስተባብሏል፤ ለከሓዲያንም ጊዜን ሰጠኋቸው። ከዚያ ቀጣኋቸው ጥላቻዬም እንዴት ነበረ (ተመልከቱ)።

فَكَأَيِّن مِّن قَرْيَةٍ أَهْلَكْنَـٰهَا وَهِىَ ظَالِمَةٌ فَهِىَ خَاوِيَةٌ عَلَىٰ عُرُوشِهَا وَبِئْرٍ مُّعَطَّلَةٍ وَقَصْرٍ
مَّشِيدٍ ﴿٤٥﴾ أَفَلَمْ يَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَتَكُونَ لَهُمْ قُلُوبٌ يَعْقِلُونَ بِهَآ أَوْ ءَاذَانٌ يَسْمَعُونَ
بِهَا ۖ فَإِنَّهَا لَا تَعْمَى ٱلْأَبْصَـٰرُ وَلَـٰكِن تَعْمَى ٱلْقُلُوبُ ٱلَّتِى فِى ٱلصُّدُورِ ﴿٤٦﴾ وَيَسْتَعْجِلُونَكَ
بِٱلْعَذَابِ وَلَن يُخْلِفَ ٱللَّهُ وَعْدَهُۥ ۚ وَإِنَّ يَوْمًا عِندَ رَبِّكَ كَأَلْفِ سَنَةٍ مِّمَّا تَعُدُّونَ ﴿٤٧﴾

**45-47.** ከከተሞች መካከል እነርሱ በደለኛ ሆነው ያጠፋናቸው እና እነርሱ በጣሪያዎቻቸው ላይ ወዳቂ የሆኑ ብዙ ናቸው። ከተራቆተም የውሃ ጉድጓድ ከተገነባም ህንፃ ያጠፋነው ብዙ ነው። ለእነርሱም በእነርሱ የሚያውቁባቸው ልቦች* ወይም የሚሰሙባቸው ጆሮዎች ይኖሯቸው ዘንድ በምድር ላይ አይሄዱምን? እነሆ ዓይኖች አይታወሩም። እነዚያ በደረቶች ውስጥ ያሉት ልቦች ግን በትክክል ይታወራሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ቀጠሮውን በፍፁም የማይጥስ ሲሆን ቅጣትን አምጣ እያሉ ያቻኩሉሃል (ያጣድፉሃል)። በጌታህ ዘንድ አንዱ ቀን ከምትቆጥሩት ቀን እንደ አንድ ሺህ ዓመት የሚመጥን ነው።

* ልብ (ቀልብ) በኢስላም ከፍተኛ ሚና አለው። በኢስላምም ከፍተኛ ትኩረት ተቸሮታል። በቁርኣንና ሐዲስም ስለልብ ብዙ ተብሏል። ነብዩም በብዙ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ ሲያወሱት ይደመጣሉ፡- «አላህ ወደ መልካችሁና ወደ ሰውነታችሁ አይመለከትም። የሚያተኩርበት ነገር ቢኖር ተግባራችሁንና ልባችሁን ነው» እውነትም ይህ አካል ወሳኝ አካል ነው። ምክንያቱም

የእሱ መበላሼት ሁሉን የሚያበላሽ፤ መስተካከሉ ሁሉንም አካል የሚያስተካክል መሆኑ በነብዩ መነገሩ ብቻ በቂ ነው። ስለዚህ ሙስሊሞች ሁልጊዜም ይህን ወሳኝ አካላችንን ከሚያበላሹ ነገሮች ሁሉ መጠበቅና መንከባከብ ያስፈልጋል። ብሎም ከታመመ ሳይውሉ ሳያድሩ ለማዳን መጣር ያስፈልጋል። እዚህ ላይ ቸል ሊባል የማይገባው ነገር ቢኖር ልቡን የሚያሳምመው ምን እንደሆነና ምንስ እንደሚያድነው የማወቁ ጉዳይ ነው። ስለዚህ ልቡን በሽተኛ ከሚያደርጉት ነገሮች ውስጥ፡-

ሀ. በሐራም መንገድ ማለት፡- በወለድ፤ በውሸት፤ በቅሚያ፤ በሥርቆት፤ በጉቦና በመሳሰለው የሐራም መንገድ የተገኘን መመገብ፤

ለ. ዝሙት መስራት፤ አስካሪ መጠጦችን መጠጣት፤ ሐሜተኝነት፤ አሉቧልተኝነት፤

ሐ. ወደ ተከለከለ ጎሳ መመልከት፤ ወንድ የባዕድን ሴት ገላ ከድንገተኛ እይታ ውጭ (ሆነ ብሎ) ማየት፤ ሴትም የባዕድን ወንድ ገላ ከድንገተኛ እይታ ውጭ (ሆነ ብላ) ማየት ማለት ነው። እነዚህና መሰል ድርጊቶች ልኢብኑ ከሚያሳምሙት ጥቂቶች ሲሆኑ መድሐኒቶቹ ደግሞ፡-

ሀ. ቁርኣንን ማንበብ፤ ማዳመጥና ማስተንተን፤

ለ. ሞትን ሁልጊዜም ማስታወስ፤

ሐ. ባለፉት ዘመናት የነበሩ ከሓዲያን የደረሰባቸውን እልቂትና ውድመት ማስታወስ፤

መ. አላህን በብዛት ማስታወስ፤

ሠ. በየቦታው ያሉትን ችግረኞች ማለትም በበሽታ በየሆስፒታሉ እየማቀቁ ያሉ ህሙማንን፤ በየ ወህኒ ቤቱ ያሉ እስረኞችን፤ በየመንገዱ የወደቁ ረሀብተኞችን፤ በየቀኑ በተባራሪ ጥይት እያለቁ ያሉ ህዝቦችን ሁኔታ ማስታወስ ጠቃሚ ነው።

وَكَأَيِّن مِّن قَرْيَةٍ أَمْلَيْتُ لَهَا وَهِيَ ظَالِمَةٌ ثُمَّ أَخَذْتُهَا وَإِلَيَّ ٱلْمَصِيرُ ﴿٤٨﴾

**48.** ከከተማ በዳይ ሆና ጊዜ የሰጠኋትና ከዚያ የያዝኳት የቀጣኋት ብዙ ናት። የመጨረሻው መመለሻ ወደ እኔ ብቻ ነው።

قُلْ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّمَآ أَنَا۠ لَكُمْ نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٤٩﴾ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ لَهُم مَّغْفِرَةٌ وَرِزْقٌ كَرِيمٌ ﴿٥٠﴾ وَٱلَّذِينَ سَعَوْا۟ فِىٓ ءَايَـٰتِنَا مُعَـٰجِزِينَ أُو۟لَـٰٓئِكَ أَصْحَـٰبُ ٱلْجَحِيمِ ﴿٥١﴾

**49-51.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ ሰዎች ሆይ! እኔ ለእናንተ ግልጽ አስፈራሪ ብቻ ነኝ በላቸው። እነዚያም በትክክል ያመኑና መልካም ስራዎችን የሰሩ ለእነርሱ ምህርትና ያማረ ሲሳይ አላቸው። እነዚያ ከአላህ የሚያመልጡ መስሏቸው ተዐምራቶቻችንን በመንቀፍ የተጉ ሰዎች ሁሉ እነርሱ የእሳት ጓዶች ናቸው።

وَمَآ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رَّسُولٍ وَلَا نَبِىٍّ إِلَّآ إِذَا تَمَنَّىٰٓ أَلْقَى ٱلشَّيْطَـٰنُ فِىٓ أُمْنِيَّتِهِۦ فَيَنسَخُ ٱللَّهُ مَا يُلْقِى ٱلشَّيْطَـٰنُ ثُمَّ يُحْكِمُ ٱللَّهُ ءَايَـٰتِهِۦ ۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ﴿٥٢﴾

**52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት አንድንም መልዕክተኛ ወይም ነብይ* አልላክንም (ህዝቦቹ እንዲሰልሙ) ባነበበ ጊዜ ሰይጣን ግን በህዝቦቹ ልብ ውስጥ የማጥመሚያን ሀሳብ የሚጥል ቢሆን እንጅ። ወዲያውም አላህ ሰይጣን የሚጥለውን ማጥመሚያ ቃል ያስወግዳል። ከዚያ አላህ አናቅፅን ያጠነክራል (ያፀናል)። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነውና።

* የሁለቱ ልዩነት መልክተኛ (ረሱል) ማለት ወህይ የተወረደለትና ለህዝቦቹ እንዲያደርስ የታዘዘ ነቢይ ግን በማድረስ ቢታዘዝም ባይታዘዝም።

لِّيَجۡعَلَ مَا يُلۡقِي ٱلشَّيۡطَٰنُ فِتۡنَةٗ لِّلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٞ وَٱلۡقَاسِيَةِ قُلُوبُهُمۡۗ وَإِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ لَفِي شِقَاقِۭ بَعِيدٖ ٥٣ وَلِيَعۡلَمَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡعِلۡمَ أَنَّهُ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّكَ فَيُؤۡمِنُواْ بِهِۦ فَتُخۡبِتَ لَهُۥ قُلُوبُهُمۡۗ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَهَادِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٥٤

**53-54.** ሰይጣን የሚጥለውን ነገር ለእነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ላለባቸውና ልቦቻቸው ደረቆች ለሆኑት ፈተና ሊያደርግ ይጥላል። በዳዮችም ከእውነት በራቀ ጭቅጭቅ (ውዝግብ) ውስጥ ናቸው። እነዚያ እውቀትን የተሰጡት እርሱ (ቁርኣን) ከጌታህ የሆነ እውነት መሆኑን እንዲያውቁና በእርሱ እንዲያምኑ ልቦቻቸውም በእርሱ እንዲረካ (ያጠነክራል)። አላህ እነዚያን በትክክል ያመኑትን ወደ ቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ መሪ ነው።

وَلَا يَزَالُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي مِرۡيَةٖ مِّنۡهُ حَتَّىٰ تَأۡتِيَهُمُ ٱلسَّاعَةُ بَغۡتَةً أَوۡ يَأۡتِيَهُمۡ عَذَابُ يَوۡمٍ عَقِيمٍ ٥٥ ٱلۡمُلۡكُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ يَحۡكُمُ بَيۡنَهُمۡۚ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فِي جَنَّٰتِ ٱلنَّعِيمِ ٥٦ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا فَأُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عَذَابٞ مُّهِينٞ ٥٧

**55-57.** እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ሰዓቲቱ በድንገት እስከምትመጣባቸው ወይም ከደግ ነገር መካን የሆነው ቀን ቅጣት እስከሚመጣባቸው ድረስ በቁርኣን ጉዳይ ከመጠራጠር አያቆሙም። በዚያ ቀን ንግስናው የአላህ ብቻ ነው። በመካከላቸው ይፈርዳል። እነዚያም በአላህ ያመኑትና መልካም ስራዎችን የሰሩት በመደሰቻ ገነቶች ውስጥ ናቸው። እነዚያ በአላህ የካዱትና በአንቀፆቻችንም ያስተባበሉት ሁሉ እነዚያ ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አለላቸው።

**ከሐጅ ምዕራፍ ከአንቀፅ (42-57) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መልዕክተኞችና የእውነት አስተማሪዎችን ማስተባበል በሰዎች ዘንድ የተለመደ የደንቆሮዎች ተግባር ስለመሆኑ፤

2. አላህ በግፈኛ ህዝቦች ላይ የጥፋት ቅጣቱ የተለመደ መሆኑን በጉልህ ማሳየት፤
3. በጥፋታቸው ከጠፉት ህዝቦች ታሪክ መማር ተገቢ ስለመሆኑ፤
4. ችኮላ የሰው ልጅ ተፈጥሯዊ ባህሪ እንደሆነና ማቻኮል ሞኝነትና ድንቁርና ስለመሆኑ፤
5. አላህ ዘንድ ያሉ ነገሮች ሁሉ በዚህች ዓለም ካሉ ነገሮች ጋር በስም እንኳን ቢገናኙ በእውነት የተለያዩ ስለመሆናቸው፤
6. የግፍ መጨረሻው ውድቀት ስለመሆኑ፤
7. የነብያት ተልዕኮ ማስጠንቀቅና ማብሰር ብቻ ስለመሆኑ፤
8. የአማኞችም ሆነ የከሓዲያን መጨረሻ ምን እንደሚመስል በግልፅ ማስረዳት፤
9. የነብያትን ንባብ ሰይጣን ለማደናገር ያደርጋቸው የነበሩት ሙከራዎች በነብዩ (ﷺ) ብቻ የተወሰነ እንዳልነበሩ፤
10. ፊትናዎች የሚጎዱት አማኞችን ሳይሆን ልበ በሽተኞችን ብቻ እንደሆነ፤
11. አላህ የቂያማ ቀን አማኞችን ሲያከብር የሽርክ ባለቤቶችን እንደሚያዋርድ፤
12. አላህ እንዳለው ሁሉ የቁረይሽ ከሓዲያን በጥርጣሬያቸው ላይ ሲዋዥቁ በበድር እለት ማለቃቸው፤

وَٱلَّذِينَ هَاجَرُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ ثُمَّ قُتِلُوٓاْ أَوۡ مَاتُواْ لَيَرۡزُقَنَّهُمُ ٱللَّهُ رِزۡقًا حَسَنٗاۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَهُوَ خَيۡرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ﴿٥٨﴾

**58.** እነዚያ ለአላህ ሀይማኖት ሲሉ የተሰደዱና ከዚያም ሲታገሉ የተገደሉ ወይም የሞቱ አላህ መልካምን ሲሳይ በእርግጥ ይሰጣቸዋል፡፡ አላህም ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነው፡፡

ከሐጅ ምዕራፍ (58) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ጥቂት ሰዎች ወደ ነብዩ መጥተው «የተገደለ ሰው ምን ምን ምንዳ እንዳለው አውቀናል፡፡ ከእርሰዎ ጋር የሞተ ሰው ምን ምንዳ አለው»በማለት ጠየቋቸው፡፡ ይህን ጊዜ የተገደለም ሆነ የሞተ ሰው ሁሉም ምንዳ እንዳለው ለመግለፅ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት፡፡

لَيُدۡخِلَنَّهُم مُّدۡخَلٗا يَرۡضَوۡنَهُۥۗ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَعَلِيمٌ حَلِيمٞ ﴿٥٩﴾

**59.** የሚወዱትን መግቢያ ገነትን በእርግጥ ያስገባቸዋል፡፡ አላህ በእርግጥ ዐዋቂና ታጋሽ ነውና፡፡

۞ ذَٰلِكَۖ وَمَنۡ عَاقَبَ بِمِثۡلِ مَا عُوقِبَ بِهِۦ ثُمَّ بُغِيَ عَلَيۡهِ لَيَنصُرَنَّهُ ٱللَّهُۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَعَفُوٌّ غَفُورٞ ﴿٦٠﴾

**60.** (ነገሩ) ይህ ነው፡፡ ያ በተበደለበት ብጤ (መጠን) የተበቀለና ከዚያ በርሱ ላይ ግፍ የተዋለበት ሰው አላህ በእርግጥ ይረዳዋል፡፡ አላህ ይቅር ባይና

መሓሪ ነውና።

ከሐጅ ምዕራፍ (60) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሙህረም ሁለት ቀን ሲቀረው በዘመተው የአንድ ሶሃባ ቡድን ላይ ሙሽሪኮች «መቼም ሙስሊሞች በሙሃረም ወር ጦርነት እያካሂዱም» በማለት ጥቃት ሰነዘሩባቸው። ቢማፀኗቸውም እምቢ ብለው ጦርነቱን ገፉበት። ይሄኔ ሙስሊሞቹ ባደረጉት የአፀፋ መልስ ድልን ስለተቀዳጁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ሱዩጢ።

ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ يُولِجُ ٱلَّيْلَ فِى ٱلنَّهَارِ وَيُولِجُ ٱلنَّهَارَ فِى ٱلَّيْلِ وَأَنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ ﴿٦١﴾

61. ይህ የሆነው አላህ ሌሊትን በቀን ውስጥ የሚያስገባ ቀንንም በሌሊት ውስጥ የሚያስገባ ቻይ፤ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ሁሉን ተመልካች በመሆኑ ነው።

ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْحَقُّ وَأَنَّ مَا يَدْعُونَ مِن دُونِهِۦ هُوَ ٱلْبَٰطِلُ وَأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْكَبِيرُ ﴿٦٢﴾

62. ይህ የሆነው አላህ መኖሩ እውነት በመሆኑ ከርሱም ሌላ የሚገዙት ነገር ፍፁም ውሸት በመሆኑና አላህም የሁሉ በላይ ታላቅ በመሆኑ ነው።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَتُصْبِحُ ٱلْأَرْضُ مُخْضَرَّةً ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَطِيفٌ خَبِيرٌ ﴿٦٣﴾

63. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከሰማይ ውሃን ማውረዱንና ከዚያ ምድር የምትለመልም መሆኗን አላየህምን? አላህ ፍፁም ሩህሩህና ውስጠ ዐዋቂ ነውና።

لَّهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۗ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَهُوَ ٱلْغَنِىُّ ٱلْحَمِيدُ ﴿٦٤﴾

64. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሰማያት ውስጥና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። አላህ ተብቃቂና ምስጉን ነውና።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ سَخَّرَ لَكُم مَّا فِى ٱلْأَرْضِ وَٱلْفُلْكَ تَجْرِى فِى ٱلْبَحْرِ بِأَمْرِهِۦ وَيُمْسِكُ
ٱلسَّمَآءَ أَن تَقَعَ عَلَى ٱلْأَرْضِ إِلَّا بِإِذْنِهِۦٓ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ بِٱلنَّاسِ لَرَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴿٦٥﴾

65. አላህ በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ ለእናንተ የገራላችሁ መርከቦችንም በባህር ውስጥ በፈቃዱ የሚንሻለሉ ሲሆኑ (የገራላችሁ)፤ መሆኑን ሰማይንም በፈቃዱ ካልሆነ በምድር ላይ እንዳትወድቅ የሚይዛት መሆኑን አላየህምን? አላህ ለሰዎች በእርግጥ ሩህሩህና አዛኝ ነውና።

وَهُوَ ٱلَّذِىٓ أَحْيَاكُمْ ثُمَّ يُمِيتُكُمْ ثُمَّ يُحْيِيكُمْ ۗ إِنَّ ٱلْإِنسَٰنَ لَكَفُورٌ ﴿٦٦﴾

**66.** እርሱም ያ! ህያው ያደረጋችሁ ነው። ከዚያ ይገድላችኋል። ከዚያ ህያው ያደርጋችኋል። ሰው በእርግጥ በጣም ከሓዲ ነው።

لِّكُلِّ أُمَّةٖ جَعَلۡنَا مَنسَكًا هُمۡ نَاسِكُوهُۖ فَلَا يُنَٰزِعُنَّكَ فِي ٱلۡأَمۡرِۚ وَٱدۡعُ إِلَىٰ رَبِّكَۖ إِنَّكَ لَعَلَىٰ
هُدٗى مُّسۡتَقِيمٖ ٦٧ وَإِن جَٰدَلُوكَ فَقُلِ ٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا تَعۡمَلُونَ ٦٨ ٱللَّهُ يَحۡكُمُ بَيۡنَكُمۡ
يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ فِيمَا كُنتُمۡ فِيهِ تَخۡتَلِفُونَ ٦٩ أَلَمۡ تَعۡلَمۡ أَنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِۚ
إِنَّ ذَٰلِكَ فِي كِتَٰبٍۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ ٧٠

**67-70.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለየህዝቡ ሁሉ እነርሱ የሚሰሩበት የሆነን ስርዓተ ሃይማኖት አድርገናል። ስለዚህ በነገሩ አይከራከሩህ። ወደ ጌታህ መንገድም ጥራ። አንተ በእርግጥ በቅኑ መንገድ ላይ ነህና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢከራከሩህም አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው በላቸው። አላህ በትንሳኤ ቀን በዚያ ትለያዩበት (ትወዛገቡበት) በነበራችሁት ሁሉ በመካከላችሁ ይፈርዳል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማይና በምድር ውስጥ ያለን ሁሉ በእርግጥ የሚያውቅ መሆኑን አታውቅምን? ይህ በመጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበ እውነት ነው። ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።

وَيَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَمۡ يُنَزِّلۡ بِهِۦ سُلۡطَٰنٗا وَمَا لَيۡسَ لَهُم بِهِۦ عِلۡمٞۗ وَمَا لِلظَّٰلِمِينَ
مِن نَّصِيرٖ ٧١ وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُنَا بَيِّنَٰتٖ تَعۡرِفُ فِي وُجُوهِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ ٱلۡمُنكَرَۖ
يَكَادُونَ يَسۡطُونَ بِٱلَّذِينَ يَتۡلُونَ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتِنَاۗ قُلۡ أَفَأُنَبِّئُكُم بِشَرّٖ مِّن ذَٰلِكُمُۚ ٱلنَّارُ
وَعَدَهَا ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ٧٢

**71-72.** ከአላህ ሌላም ምንም ማስረጃን ያላወረደበትንና ለእነርሱም በእርሱ እውቀት የሌላቸውን ነገር ይገዛሉ፤ ለበዳዮች ምንም ረዳት የላቸውም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንቀፆቻችን የተብራሩ ሆነው በእነርሱ ላይ በሚነበቡ ጊዜ በእነዚያ በአላህ በካዱት ሰዎች ፊት ላይ ጥላቻን ታውቃለህ። በእነዚያ ላይ አንቀፆቻችንን በሚያነቡት ላይም በኃይል ሊዘልሉባቸው ይቃረባሉ። ይልቅ ከዚህ የከፋን ነገር ልንገራችሁን? እርሷም እሳት ናት። አላህ ለእነዚያ በሱ ለካዱት ሰዎች ሁሉ ቀጥሯታል፤ መመለሻነቷ ምን ይከፋ በላቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ضُرِبَ مَثَلٞ فَٱسۡتَمِعُواْ لَهُۥٓۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَن يَخۡلُقُواْ

ذُبَابًا وَلَوِ ٱجْتَمَعُوا۟ لَهُۥ ۖ وَإِن يَسْلُبْهُمُ ٱلذُّبَابُ شَيْـًٔا لَّا يَسْتَنقِذُوهُ مِنْهُ ۚ ضَعُفَ ٱلطَّالِبُ
وَٱلْمَطْلُوبُ ﴿٧٣﴾ مَا قَدَرُوا۟ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦٓ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَقَوِىٌّ عَزِيزٌ ﴿٧٤﴾

73-74. ሰዎች ሆይ! አስደናቂ ምሳሌ ተገለፀላችሁ። ለእርሱም አድምጡት፤ እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣዖታት ሁሉ ዝንብን ለመፍጠር ቢሰበሰቡ ፈፅሞ መፍጠር እንኳ አይችሉም። አንዳችንም ነገር ዝንብ ቢነጥቃቸው ከእርሱ አያስጥሉትም። ፈላጊውም (አምላኪው) ተፈላጊውም (ተመላኪው) ደከሙ። አላህን ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም። አላህ በጣም ሀያልና አሸናፊ ነውና።

ٱللَّهُ يَصْطَفِى مِنَ ٱلْمَلَـٰٓئِكَةِ رُسُلًا وَمِنَ ٱلنَّاسِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ ﴿٧٥﴾

75. አላህ ከመላእክት ውስጥ መልዕክተኞችን ይመርጣል። ከሰዎችም መካከል እንደዚሁ መልዕክተኞችን ይመርጣል። አላህ የሚባለውን ሁሉ ሰሚ ሁሉን ተመልካች ነው።

يَعْلَمُ مَا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ ۗ وَإِلَى ٱللَّهِ تُرْجَعُ ٱلْأُمُورُ ﴿٧٦﴾

76. በስተፊታቸውም ሆነ በስተኋላቸው ያለን ሁሉ ያውቃል። ወደ አላህም ነገሮች ሁሉ ይመለሳሉ።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱرْكَعُوا۟ وَٱسْجُدُوا۟ وَٱعْبُدُوا۟ رَبَّكُمْ وَٱفْعَلُوا۟ ٱلْخَيْرَ لَعَلَّكُمْ
تُفْلِحُونَ ۩ ﴿٧٧﴾ وَجَـٰهِدُوا۟ فِى ٱللَّهِ حَقَّ جِهَادِهِۦ ۚ هُوَ ٱجْتَبَىٰكُمْ وَمَا جَعَلَ عَلَيْكُمْ فِى
ٱلدِّينِ مِنْ حَرَجٍ ۚ مِّلَّةَ أَبِيكُمْ إِبْرَٰهِيمَ ۚ هُوَ سَمَّىٰكُمُ ٱلْمُسْلِمِينَ مِن قَبْلُ وَفِى هَـٰذَا لِيَكُونَ
ٱلرَّسُولُ شَهِيدًا عَلَيْكُمْ وَتَكُونُوا۟ شُهَدَآءَ عَلَى ٱلنَّاسِ ۚ فَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُوا۟ ٱلزَّكَوٰةَ
وَٱعْتَصِمُوا۟ بِٱللَّهِ هُوَ مَوْلَىٰكُمْ ۖ فَنِعْمَ ٱلْمَوْلَىٰ وَنِعْمَ ٱلنَّصِيرُ ﴿٧٨﴾

77-78. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ከአላህ ቁጣ ትድኑ ዘንድ በስግደታችሁ አጎንብሱ። በግንባራችሁም ላይ ተደፉ (ሩኩዕና ሱጁድ አድርጉ) ጌታችሁንም በትክክል ተገዙት። በጎንም ነገር ስሩ ልትድኑ ይከጀልላችኋልና። በአላህ ሃይማኖት ተገቢውን ትግል ታገሉ። እርሱ መርጧችኋል። በናንተም ላይ በሃይማኖቱ ውስጥ ምንም ችግር አላደረገባችሁም። የአባታችሁን የኢብራሂምን ሃይማኖት ተከተሉ። እርሱ ከዚህ በፊት ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል። በዚህ ቁርኣንም መልዕክተኛው

በእናንተ ላይ መስካሪ እንዲሆን እናንተም በሰዎች ላይ መስካሪዎች እንድትሆኑ ሙስሊሞች ብሎ ሰይሟችኋል። ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ። ዘካንም በአግባቡ ለተገቢው ስጡ። በአላህም ተጠበቁ። እርሱ ረዳታችሁ ነውና። እርሱ ምን ያምር ጠባቂ ምን ያምርም ረዳት ነው።

**ከሐጅ ምዕራፍ ከአንቀፅ (58-78) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ለአላህ ብሎ የሚደረጉ ስደቶች ጂሀድን የሚስተካከሉ መሆናቸውን፤
2. አፀፋ መስጠት ቢፈቀድም ይቅር ማለቱ ግን እንደሚበልጥ፤
3. የአላህን ጌትነትና ባህሪያት በጥቂቱ፤
4. ከአላህ ባህሪያቶች አልፎ አልፎ መጥቀስ፤
5. ተውሒድን ማረጋገጥ፤
6. ሰላትና ዘካ ግዴታ ስለመሆናቸው፤
7. አላህ ለፍጡሮች የዋላቸውን ፀጋዎች ማስታወስ፤
8. የአላህን ችሎታ የሚያሳዩ ክስተቶችን ማንሳት፤
9. ህዝቦች ሁሉ መልዕክተኛ እንደተላከላቸው ማረጋገጥ፤
10. ግልፅ በሆኑ ነገሮች ላይ ክርክርና ጭቅጭቅን መተው እንደሚወደድ
11. የቀድርን ጉዳይ ማስተማር፤
12. ከሓዲያን ለሙዕሚኖች ያላቸው ጥላቻ በተለይም በሚያስተምሯቸው ጊዜ እንደሚበረታ፤
13. ግፈኛን ሊያስቆጣው በሚችል ነገር ማስቆጣት ተገቢ ስለ መሆኑ፤
14. በትምህርት ጊዜ ምሳሌዎችን መጥቀስ እንደሚወደድ፤
15. ሽርክንና ባለቤቶቹን ማውገዝ፤
16. በአላህ ጣኦታትን ያጋራ አላህን በአግባቡ እንዳልተገዛ፤
17. መልዕክተኝነት ለመልአክዎች እንደሚሆን፤
18. የሶላትን አምልኮትና የመልካምንም ስራ ትልቅነት፤
19. ስለ ጂሀድ ትልቅነትና ትክክለኛ ሙእሚን ማለት ስለ አላህ ይሉኝታ የማይዘው መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የሐጅ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (23)
# የአማኞች ምዕራፍ
# (ሱረቱ አልሙእሚኑን)

سُورَةُ المُؤْمِنُونَ

## የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (118) ናቸው።

## የሱረቱ አል ሙእሚኑን መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ሱረቱ አልሙእሚኑን፤ ሱረቱ ቀድ አፍላህ፤ ሱረቱ አልፈላህ በመባልም ይታወቃል። በመግቢያው ላይ ምእመናን የፈለጉትን እንደሚያገኙ በማብሰርና የአማኞችን ባህሪ በመዘርዘር ይጀምራል። በመቀጠል የአላህ ችሎታ ከሚታይባቸው ፍጥረታቱ ጥቂቶቹን ይጠቅሳል። ከእነዚህም መካከል አላህ ሰውን እንዴት እንደፈጠረ ማየቱ ብቻ በቂ እንደሆነና አላህ የተለያዩ ጥያቄዎችን በማቅረብ እንዲያምኑት ከማድረጉም አልፎ ሰዎች የትንሳኤ እለት ለምርምራ እንደሚቀርቡ ጉዳታቸውም በፍትህ እንደሚታይላቸው ያስተምረናል። በመጨረሻም የአላህን ትልቅነት በማስገንዘብ ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

قَدۡ أَفۡلَحَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ﴿١﴾ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي صَلَاتِهِمۡ خَٰشِعُونَ ﴿٢﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَنِ ٱللَّغۡوِ
مُعۡرِضُونَ ﴿٣﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِلزَّكَوٰةِ فَٰعِلُونَ ﴿٤﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِفُرُوجِهِمۡ حَٰفِظُونَ ﴿٥﴾ إِلَّا عَلَىٰٓ
أَزۡوَٰجِهِمۡ أَوۡ مَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُهُمۡ فَإِنَّهُمۡ غَيۡرُ مَلُومِينَ ﴿٦﴾ فَمَنِ ٱبۡتَغَىٰ وَرَآءَ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ
هُمُ ٱلۡعَادُونَ ﴿٧﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِأَمَٰنَٰتِهِمۡ وَعَهۡدِهِمۡ رَٰعُونَ ﴿٨﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَلَىٰ صَلَوَٰتِهِمۡ
يُحَافِظُونَ ﴿٩﴾ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡوَٰرِثُونَ ﴿١٠﴾ ٱلَّذِينَ يَرِثُونَ ٱلۡفِرۡدَوۡسَ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿١١﴾

**1-11.** ምዕምናን ፍላጎታቸውን ሁሉ በእርግጥ አገኙ (ምዕምናን ተሳካላቸው) ዳኑ። እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ውስጥ አላህን ፈሪዎች የሆኑ፤ እነዚያ እነርሱ ከመጥፎ ነገር ሁሉ የራቁ። እነዚያ እነርሱ ዘካን በአግባቡ ሰጪዎች፤ እነዚያ እነርሱ በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዟቸው ሴት ባሪያዎች ላይ ሲቀር ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት፤ እነርሱ በእነዚህ የማይወቀሱ ናቸውና። ከዚህ ሌላ በሆነ መንገድ የፈለጉ ሰዎች እነዚያ እነርሱ የአላህን ወሰን አላፊዎች ናቸው። እነዚያም እነርሱ ለአደራዎቻቸውና ለቃል ኪዳናቸው ጠባቂዎች፣ እነዚያ እነርሱ በስግደቶቻቸው ላይ አላህን የሚጠባበቁ፣ የሆኑት እነዚያ ወራሾቹ እነርሱ ናቸው፤ እነዚያ ፊርደውስን (ላዕላይ ገነትን)፤ የሚወርሱ ናቸው። እነርሱ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች እነርሱ ብቻ ናቸው።*

* ነብዩ (ﷺ) ወህይ ሲወርድላቸው ከአጠገባቸው የንብ መንጋ አይነት ድምፅ ይሰማ ነበር። አንድ ቀን ወህይ ወርዶ አንድ ሰዓት እንደቆየን ነብዩ ወደ ቂብላ ፊታቸውን አዙረው እጃቸውን ወደ ሰማይ በማንሳት «ጌታዬ ጨምርልን አታጉድልብን! አክብረን አታዋርደን! ስጠን አትከልክለን ለእኛ ቅድሚያ ስጠን አታስቀድመን! ውደድልን አስወድደን! በማለት ዱዓ አደረጉ። ከዚያም «በዛሬው ዕለት የተገበሯቸውን ሰዎች ሁሉ ጀነት የሚያስገቡ አስር አናቅፅ ወረዱ» ካሉ በኋላ እነዚህን አናቅፅ አነበቡ። (አህመድ፤ ቲርሚዚና ነሳኢ)

እናታችን ዓኢሻ «የነብዩ ባህሪ ምን ይመስል ነበር» ተብለው ሲጠየቁ «ባህሪያቸው ቁርኣን ነበር» ካሉ በኋላ እነዚህን አናቅፅ አነበቡና የነብዩ ባህሪ እንዲህ ነበር አሉ። (ነሳኢ)

وَلَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ مِن سُلَٰلَةٖ مِّن طِينٖ ﴿١٢﴾ ثُمَّ جَعَلۡنَٰهُ نُطۡفَةٗ فِي قَرَارٖ مَّكِينٖ ﴿١٣﴾
ثُمَّ خَلَقۡنَا ٱلنُّطۡفَةَ عَلَقَةٗ فَخَلَقۡنَا ٱلۡعَلَقَةَ مُضۡغَةٗ فَخَلَقۡنَا ٱلۡمُضۡغَةَ عِظَٰمٗا فَكَسَوۡنَا
ٱلۡعِظَٰمَ لَحۡمٗا ثُمَّ أَنشَأۡنَٰهُ خَلۡقًا ءَاخَرَۚ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ أَحۡسَنُ ٱلۡخَٰلِقِينَ ﴿١٤﴾

**12-14.** ሰውን አደምን ከነጠረ ጭቃ ፈጠርነው። ከዚያ በተጠበቀ መርጊያ ውስጥ የፍትወት ጠብታ አደረግነው። ከዚያ ጠብታዋን (በአርባ ቀን) የረጋ ደም አድርገን ፈጠርን። የረጋውንም ደም ቁራጭ ስጋ አድርገን ፈጠርን፤ ቁራጭዋንም ስጋ አጥንቶች አድርገን ፈጠርን፤ አጥንቶችንም ስጋን አለበስናቸው። ከዚያ (ነፍስን በመዝራት) ሌላ ፍጥረት አድርገን አስገኘነው። ከሰዓሊዎችም ሁሉ በላጭ የሆነው አላህ ላቀ።

ከአማኞች ምዕራፍ (14) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዑመር ኢብኑ አልኸጣብ ይህን ቃል ሲናገሩ የእሳቸው አባባል ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ثُمَّ إِنَّكُم بَعۡدَ ذَٰلِكَ لَمَيِّتُونَ ﴿١٥﴾ ثُمَّ إِنَّكُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ تُبۡعَثُونَ ﴿١٦﴾

**15-16.** (ሰዎች ሆይ!) ከዚያም እናንተ ከዚህ በኋላ በእርግጥ ሟቾች ናችሁ። ከዚያ እናንተ በትንሳኤ ዕለት ትቀሰቀሳላችሁ።

وَلَقَدۡ خَلَقۡنَا فَوۡقَكُمۡ سَبۡعَ طَرَآئِقَ وَمَا كُنَّا عَنِ ٱلۡخَلۡقِ غَٰفِلِينَ ﴿١٧﴾ وَأَنزَلۡنَا مِنَ ٱلسَّمَآءِ
مَآءَۢ بِقَدَرٖ فَأَسۡكَنَّٰهُ فِي ٱلۡأَرۡضِۖ وَإِنَّا عَلَىٰ ذَهَابِۭ بِهِۦ لَقَٰدِرُونَ ﴿١٨﴾ فَأَنشَأۡنَا لَكُم بِهِۦ
جَنَّٰتٖ مِّن نَّخِيلٖ وَأَعۡنَٰبٖ لَّكُمۡ فِيهَا فَوَٰكِهُ كَثِيرَةٞ وَمِنۡهَا تَأۡكُلُونَ ﴿١٩﴾ وَشَجَرَةٗ تَخۡرُجُ
مِن طُورِ سَيۡنَآءَ تَنۢبُتُ بِٱلدُّهۡنِ وَصِبۡغٖ لِّلۡأٓكِلِينَ ﴿٢٠﴾ وَإِنَّ لَكُمۡ فِي ٱلۡأَنۡعَٰمِ لَعِبۡرَةٗۖ نُّسۡقِيكُم
مِّمَّا فِي بُطُونِهَا وَلَكُمۡ فِيهَا مَنَٰفِعُ كَثِيرَةٞ وَمِنۡهَا تَأۡكُلُونَ ﴿٢١﴾
وَعَلَيۡهَا وَعَلَى ٱلۡفُلۡكِ تُحۡمَلُونَ ﴿٢٢﴾

**17-22.** በእርግጥም ከበላያችሁ ሰባትን ሰማያት ፈጠርን። ከፍጥረቶቹም ዝንጉዎች አይደለንም። ከሰማይም ውሃን በልክ አወረድን። በምድርም ውስጥ አስቀመጥነው። እኛም እርሱን በማስወገድ ላይ በእርግጥ ቻዮች ነን። በእርሱም የዘምባባዎችና የወይኖች አትክልቶችን ለእናንተ አስገኘንላችሁ። በውስጧ ለእናንተ ብዙ ፍራፍሬዎች አሏችሁ። ከእርሷም ትበላላችሁ። ከሲና ተራራ የምትወጣ ዛፍ በቅባትና ለበይዎች መባያ በሚሆን ዘይት ተቀላቅላ የምትበቅልን አስገኘንላችሁ። (ሰዎች ሆይ!) እናንተም በግመል፤ በከብት በፍየልና በበግ መገምገሚያ አላችሁ። በሆዶችዋ ውስጥ ካለው ወተት እናጠጣችኋለን። ለእናንተም በእርሷ ብዙ ጥቅሞች አሏችሁ። ከእርሷም ትበላላችሁ። በእሷ ላይና በመርከብም ላይ ትጫናላችሁ።

**ከአማኞች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-22) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ሶላት በፍርሀት መስገድ እንዳለበት፣
2. የጊዜያዊ ጋብቻ ክልክል ስለ መሆኑ፣
3. የዘር ስሜትን በእጅ ማፍሰስ የተከለከለ ስለ መሆኑ፣
4. ዘካን መስጠት፣ አማናን መጠበቅ በቃል መሙላት እና ሶላቶችን ጊዜያቸውን ጠብቆ መስገድ ግዴታ ስለመሆኑ፣
5. የጀነትና የጀሀነም ሰዎች በራሳቸው እንደሚወራረሱ፣
6. የአላህ ችሎታና ጥበብ መገለጫ ከስተቶችና የአላህን ኃያልነትና ችሎታ በግልፅ ማረጋገጥ፣
7. የሰው ልጅ አፈጣጠር እና ያለፈባቸው ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉ፣
8. የሰው ልጅ ከተፈጠረ በኋላ ምን እንደሚሆን፣
9. ሙቶ መነሳትን በልዩ ልዩ መረጃዎች እንደሚረጋገጥ፣
10. አላህ ሊመስገን የሚገባው ስለ መሆን፣
11. አላህ ውሃን በልክ በማውረድ የዋለውን ታላቅ ውለታ እንድናስታውስ ማድረግ፣
12. የዘይትን ጥቅሞች እንድናጤን ማድረግ፣
13. አላህ እንሰሳቶችንና መርከቦችን ፈጥሮ ለልዩ ልዩ ጥቅሞች እንድናውላቸው ማስቻሉን፣

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ فَقَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥٓۚ أَفَلَا
تَتَّقُونَ ﴿٢٣﴾ فَقَالَ ٱلۡمَلَؤُاْ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن قَوۡمِهِۦ مَا هَٰذَآ إِلَّا بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡ يُرِيدُ أَن
يَتَفَضَّلَ عَلَيۡكُمۡ وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَأَنزَلَ مَلَٰٓئِكَةٗ مَّا سَمِعۡنَا بِهَٰذَا فِيٓ ءَابَآئِنَا ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٢٤﴾
إِنۡ هُوَ إِلَّا رَجُلُۢ بِهِۦ جِنَّةٞ فَتَرَبَّصُواْ بِهِۦ حَتَّىٰ حِينٖ ﴿٢٥﴾ قَالَ رَبِّ ٱنصُرۡنِي بِمَا كَذَّبُونِ ﴿٢٦﴾
فَأَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡهِ أَنِ ٱصۡنَعِ ٱلۡفُلۡكَ بِأَعۡيُنِنَا وَوَحۡيِنَا فَإِذَا جَآءَ أَمۡرُنَا وَفَارَ ٱلتَّنُّورُ فَٱسۡلُكۡ
فِيهَا مِن كُلّٖ زَوۡجَيۡنِ ٱثۡنَيۡنِ وَأَهۡلَكَ إِلَّا مَن سَبَقَ عَلَيۡهِ ٱلۡقَوۡلُ مِنۡهُمۡۖ وَلَا تُخَٰطِبۡنِي فِي
ٱلَّذِينَ ظَلَمُوٓاْ إِنَّهُم مُّغۡرَقُونَ ﴿٢٧﴾ فَإِذَا ٱسۡتَوَيۡتَ أَنتَ وَمَن مَّعَكَ عَلَى ٱلۡفُلۡكِ فَقُلِ ٱلۡحَمۡدُ
لِلَّهِ ٱلَّذِي نَجَّىٰنَا مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢٨﴾ وَقُل رَّبِّ أَنزِلۡنِي مُنزَلٗا مُّبَارَكٗا وَأَنتَ خَيۡرُ
ٱلۡمُنزِلِينَ ﴿٢٩﴾ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ وَإِن كُنَّا لَمُبۡتَلِينَ ﴿٣٠﴾

**23-30.** ኑሕን ወደ ህዝቦቹ በእርግጥ ላክነው። ወዲያውም ህዝቦቼ ሆይ! አላህን ብቻ ተገዙ። ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ ምንም አምላክ የላችሁም። አትጠነቀቁምን? አላቸው። ከህዝቦቿም እነዚያ ታላላቆቹ ሰዎች ይህ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ አይደለም። በእናንተ ላይ መብለጥን ይፈልጋል። አላህ ቢፈልግ ኖሮ መላእክትን ባወረደ ነበር። ይህንንም የሚለውን በመጀመሪያዎቹ አባቶቻችን አልሰማንም። እርሱ እብደት ያለበት ሰው

እንጂ ሌላ አይደለም። በእርሱም እስከ ሞቱ ጊዜ ድረስ ተጠባበቁ አሉ። ኑሕም ጌታዬ ሆይ! ስለ አስተባበሉኝ እርዳኝ አለ። ወደ እርሱ እንዲህ ስንል ላክን። በተመልካችነታችንና በትእዛዛችን ታንኳን ስራ። ከዚያ ትእዛዛችን በመጣና ምድጃው (እቶኑ) በፈለቀ ጊዜ በውስጧ ከሁሉም ነገር ሁለት ሁለት ዓይነቶችንና ቤተሰቦችህን ከእነርሱ መካከል ጠፊ በመሆኑ ቃል ያለፈበት ብቻ ሲቀር አስገባ። በእነዚያ ራሳቸውን በአላህ በመካድ በበደሉት ሰዎች ጉዳይ አታነጋግረኝ። እነርሱ በውኃ ተሰማጪዎች (ተሰጣሚዎች) ናቸውና። አንተም አብረውህ ካሉት ፍጡሮች ጋር በታንኳይቱ ላይ በተደላደልክ ጊዜ ምስጋና ሁሉ ለዚያ ከበደለኛ ህዝቦች ላዳነን አላህ ይገባው በል። ጌታዬ ሆይ፤ ብሩክ የሆነን ማውረድ አውርደኝ። አንተም ከአውራጆች ሁሉ በላጭ ነህና" በል። በዚህ ውስጥ ለሃያልነታችን ተዐምራቶች አሉበት። እነሆ እኛ የኑሕን ሰዎች ፈታኞች ነበርን።

ثُمَّ أَنشَأۡنَا مِنۢ بَعۡدِهِمۡ قَرۡنًا ءَاخَرِينَ ٣١ فَأَرۡسَلۡنَا فِيهِمۡ رَسُولٗا مِّنۡهُمۡ أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مَا لَكُم
مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرُهُۥٓۚ أَفَلَا تَتَّقُونَ ٣٢ وَقَالَ ٱلۡمَلَأُ مِن قَوۡمِهِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَكَذَّبُواْ بِلِقَآءِ ٱلۡأٓخِرَةِ
وَأَتۡرَفۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا مَا هَٰذَآ إِلَّا بَشَرٞ مِّثۡلُكُمۡ يَأۡكُلُ مِمَّا تَأۡكُلُونَ مِنۡهُ وَيَشۡرَبُ
مِمَّا تَشۡرَبُونَ ٣٣ وَلَئِنۡ أَطَعۡتُم بَشَرٗا مِّثۡلَكُمۡ إِنَّكُمۡ إِذٗا لَّخَٰسِرُونَ ٣٤ أَيَعِدُكُمۡ أَنَّكُمۡ إِذَا
مِتُّمۡ وَكُنتُمۡ تُرَابٗا وَعِظَٰمًا أَنَّكُم مُّخۡرَجُونَ ٣٥ ۞هَيۡهَاتَ هَيۡهَاتَ لِمَا تُوعَدُونَ ٣٦ إِنۡ هِيَ إِلَّا
حَيَاتُنَا ٱلدُّنۡيَا نَمُوتُ وَنَحۡيَا وَمَا نَحۡنُ بِمَبۡعُوثِينَ ٣٧ إِنۡ هُوَ إِلَّا رَجُلٌ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبٗا وَمَا
نَحۡنُ لَهُۥ بِمُؤۡمِنِينَ ٣٨ قَالَ رَبِّ ٱنصُرۡنِي بِمَا كَذَّبُونِ ٣٩ قَالَ عَمَّا قَلِيلٖ لَّيُصۡبِحُنَّ نَٰدِمِينَ ٤٠
فَأَخَذَتۡهُمُ ٱلصَّيۡحَةُ بِٱلۡحَقِّ فَجَعَلۡنَٰهُمۡ غُثَآءٗۚ فَبُعۡدٗا لِّلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ٤١

**31-41.** ከዚያ ከኋላቸው ሌሎችን የክፍለ ዘመናት ህዝቦች አስገኘን። በውስጣቸውም ከእነርሱ የሆነን መልዕክተኛ አላህን ተገዙ ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ አምላክ የላችሁም። አትጠነቀቁምን? በማለት ላክን። ከህዝቦቹም እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች በመጨረሻይቱም ቀን መገናኘት ያስተባበሉት በቅርቢቱም ህይወት ያቀማጠልናቸው ታላላቅ ሰዎች ይህ ብጤያችሁ ሰው እንጂ ሌላ አይደለም። ከምትበሉት ምግብ ይበላል፤ ከምትጠጡትም ውሃ ይጠጣል አሉ። የናንተው ብጤያችሁ የሆነን ሰው ብትታዘዙ በእርግጥ የተሞኛችሁ ናችሁ አሉ። እናንተ ሞታችሁ ዐፈርና አጥንቶችም በሆናችሁ ጊዜ እናንተ

ከመቃብር ትወጣላችሁ በማለት ያስፈራራችኋልን? ያ የምትስፈራሩበት ነገር ከእውነት ራቀ፤ በጣም ራቀ እርሷ። (ህይወት) ማለት ቅርቢቱ ህይወታችን ብቻ እንጂ ሌላ አይደለችም። እንሞታለን። (ልጆቻችን ስለሚተኩ ደግሞ) ህያውም እንሆናለን። እኛም ፈፅሞ ተቀስቃሾች አይደለንም። እርሱ በአላህ ላይ ውሸትን የቀጠፈ ሰው እንጂ ሌላ አይደለም። እኛም በእርሱ አማኞች አይደለንም አሉ። መልዕክተኛውም ጌታዬ ሆይ! ስላስተባበሉኝ በእነርሱ ላይ እርዳኝ አለ። አላህም ከጥቂት ጊዜ በኋላ በጥፋታቸው በእርግጥ ተጸጻቾች ይሆናሉ አለው። ወዲያውም (የጥፋት) ጩኸቲቱ በእውነት ያዘቻቸው፤ እንደ ጎርፍ ግብስባሽም አደረግናቸው። ለበደለኞች ህዝቦችም ከእዝነት መራቅ ተገባቸው።

ثُمَّ أَنشَأْنَا مِنۢ بَعْدِهِمْ قُرُونًا ءَاخَرِينَ ﴿٤٢﴾ مَا تَسْبِقُ مِنْ أُمَّةٍ أَجَلَهَا وَمَا يَسْتَـْٔخِرُونَ ﴿٤٣﴾

**42-43.** ከዚያም ከእነርሱ በኋላ ሌሎችን የክፍለ ዘመናት ህዝቦች አስገኘን። ማንኛይቱም ህዝብ ጊዜዋን አትቀድምም። ከጊዜያቸውም አይቆዩምም።

ثُمَّ أَرْسَلْنَا رُسُلَنَا تَتْرَا ۖ كُلَّ مَا جَآءَ أُمَّةً رَّسُولُهَا كَذَّبُوهُ ۚ فَأَتْبَعْنَا بَعْضَهُم بَعْضًا وَجَعَلْنَـٰهُمْ أَحَادِيثَ ۚ فَبُعْدًا لِّقَوْمٍ لَّا يُؤْمِنُونَ ﴿٤٤﴾

**44.** ከዚያም መልዕክተኞቻችንን በተከታታይ ላክን፤ ማንኛይቱንም ህዝብ መልእክተኛዋ በመጣላት ቁጥር አስተባበሉት ከፊላቸውንም በከፊሉ በጥፋት አስከታተልን፤ ወሬዎችም አደረግናቸው፤ ለማያምኑም ህዝቦች ከእዝነታችን መራቅ ተገባቸው።

ثُمَّ أَرْسَلْنَا مُوسَىٰ وَأَخَاهُ هَـٰرُونَ بِـَٔايَـٰتِنَا وَسُلْطَـٰنٍ مُّبِينٍ ﴿٤٥﴾ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ وَمَلَإِيْهِۦ فَٱسْتَكْبَرُوا۟ وَكَانُوا۟ قَوْمًا عَالِينَ ﴿٤٦﴾ فَقَالُوٓا۟ أَنُؤْمِنُ لِبَشَرَيْنِ مِثْلِنَا وَقَوْمُهُمَا لَنَا عَـٰبِدُونَ ﴿٤٧﴾ فَكَذَّبُوهُمَا فَكَانُوا۟ مِنَ ٱلْمُهْلَكِينَ ﴿٤٨﴾ وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَـٰبَ لَعَلَّهُمْ يَهْتَدُونَ ﴿٤٩﴾

**45-49.** ከዚያ ሙሳንና ወንድሙን ሃሩንን በተአምራታችንና በግልጽ ማስረጃ ላክናቸው። ወደ ፈርዖንና ወደ ጭፍሮቹ ላክናቸው። ድሮውንም፤ የተንበጣረሩ ህዝቦችም ነበሩ። ብጤያችንም ለሆኑት ሁለት ሰዎች ህዝቦቻቸው ለኛ ተገዢዎች ሆነው ሳሉ እናምናለን? አሉ። አስተባበሏቸውም፤ ከጠፊዎችም ሆኑ። ሙሳንም ነገዶቹ ይመሩ ዘንድ መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው።

وَجَعَلۡنَا ٱبۡنَ مَرۡيَمَ وَأُمَّهُۥٓ ءَايَةٗ وَءَاوَيۡنَٰهُمَآ إِلَىٰ رَبۡوَةٖ ذَاتِ قَرَارٖ وَمَعِينٖ ۝٥٠

**50.** የመርየምን ልጅ ዒሳንና እናቱንም ተዐምር አደረግናቸው። የመደላደልና የምንጭ ባለቤት ወደ ሆነች ከፍተኛ ስፍራም አስጠጋናቸው።

**ከአማኞች ምዕራፍ ከአንቀፅ (23-50) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የታላቁን የነቢዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
2. የነብይነት ጥሪ አንድ አይነትና ወደ ተውሒድ እንደነበር፤
3. ሁልጊዜ እውነትን የሚቃወሙ ሀብታሞችና ገዢ መሪዎች ስለ መሆናቸው፤
4. ግፈኞች የእውነትን ጥሪ ለመቃወም የሚጠቀሟቸው አሉባልታዎች ከእውነት የራቁ መሆናቸውን።
5. ወህይንና የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
6. በታሪክ የታወቀውን የኑህ ዘመን የማዕበል ቅጣት ማረጋገጥ፤
7. የግፍና የግፈኞችን መጨረሻ በግልፅ ማሳየት፤
8. የትራንስፓርት መጓጓዣዎችን ለመጠቀም ስናስብ ይህን ሱና ማድረግ ተገቢ እንደሆነ፤
9. ታሪኮችን የመመዝገብ ጥቅም ምን እንደሆነ መጥቀስ
10. አላህ ነብያትን የመላከ ተለምዶና የነብያት ሁሉ የመጀመሪያ ጥሪ ወደ ላኢላሃ ኢለላህ እንደነበር፤
11. የኩፍር ባለቤቶች ሁል ጊዜም ተንኮልን እንደ ደግ ነገር እንደሚያስቡ፤
12. ምቾት ለብዙ መጥፎ ነገሮች ምክንያት ስለሆነ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ፤
13. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
14. ብዙ ከሓዲያን ሀቅን ላለመቀበል ይከላከሉበት የነበረው ምክንያት መልዕክተኛ እንዴት ሰው ይሆናል? የሚለው እንደነበር፤
15. አላህ የተበደሉ ሰዎችን ፀሎት በተለይም የመልካም ሰዎችን እንደማይመልስ፤
16. የህዝቦችም ሆነ የግለሰቦች እድሜ ከተወሰነለት ሰዓት መቅደምም ሆነ መዘግየት እንደማይችል፤
17. ካለፉት ህዝቦች መካከል አላህ ቅጣት ሲያመጣ ነፃ የወጡት አማኞች ብቻ ስለ መሆናቸው፤
18. የነብዩ (ﷺ) ኡመት ትልቅ ስለ መሆኑ፤
19. የሙሳንና የወንድማቸው የሀሩን ነብይነትን ማረጋገጥ፤
20. ኩራትን ማውገዝና ኩራትም ሐቅን ላለመቀበል ዋና ምክንያት ስለመሆኑ፤
21. የአላህን ችሎታና እውቀት የሚያሳዩ ክንውኖች፤
22. የነብዩ ዒሳ ያለ አባት መወለድ አላህ ሰዎችን ከሞት በኋላ መቀስቀስ እንደሚችል የሚያሳይ ክስተት መሆኑን፤

يَٰٓأَيُّهَا ٱلرُّسُلُ كُلُواْ مِنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَٱعۡمَلُواْ صَٰلِحًاۖ إِنِّي بِمَا تَعۡمَلُونَ عَلِيمٞ ۝٥١

**51.** እናንተ መልእክተኞች ሆይ፣ ከተፈቀዱት ምግቦች ሁሉ ብሉ። በጎ ስራንም ስሩ። እኔ የምትሰሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነኝና።

وَإِنَّ هَٰذِهِۦٓ أُمَّتُكُمْ أُمَّةً وَٰحِدَةً وَأَنَا۠ رَبُّكُمْ فَٱتَّقُونِ ﴿٥٢﴾ فَتَقَطَّعُوٓا۟ أَمْرَهُم بَيْنَهُمْ زُبُرًا ۖ كُلُّ حِزْبٍۭ بِمَا لَدَيْهِمْ فَرِحُونَ ﴿٥٣﴾ فَذَرْهُمْ فِى غَمْرَتِهِمْ حَتَّىٰ حِينٍ ﴿٥٤﴾

**52-54.** ይህችም በአንድ አምላክ የማመን ህግጋት አንድ መንገድ ስትሆን ሃይማኖታችሁ ናት። እኔም ጌታችሁ ነኝና ፍሩኝ። ከዚያ ተከታዮቻቸው ሃይማኖታቸውን በመካከላቸው ክፍልፍሎች አድርገው ቆራረጡ፤ ህዝቦች ሁሉ እነርሱ ዘንድ ባለው ሃይማኖት ተደሳቾች ናቸው።* እስከ ጊዜያቸውም ድረስ በጥመታቸው ውስጥ ተዋቸው።

✶ ቲርሚዚይ፤ ኢብኑ ማጃህ እና አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አይሁዶችና ክርስቲያኖች ለሰባ አንድ ወይም ለሰባ ሁለት ቦታ ይከፋፈላሉ። ይህ ሕዝብ ደግሞ ለሰባ ሶስት ቦታ ይከፋፈላል። ከአንዱ በስተቀር ሁሉም የጀሀነም ናቸው። ያም አንዱ መንገድ እኔና ሱሓባዎቼ ያለንበት ነው።»

أَيَحْسَبُونَ أَنَّمَا نُمِدُّهُم بِهِۦ مِن مَّالٍ وَبَنِينَ ﴿٥٥﴾ نُسَارِعُ لَهُمْ فِى ٱلْخَيْرَٰتِ ۚ بَل لَّا يَشْعُرُونَ ﴿٥٦﴾

**55-56.** ከገንዘብና ከልጆች በእርሱ እንድንጨምርላቸው ያስባሉን? በበጎ ነገሮች ሁሉ የምንቻኮልላቸው መሆኑን ያስባሉን? አይደለም፤ ይህ ሁሉ እነርሱን ለማዘናጋት መሆኑን አያውቁም።*

✶ ትክክለኛ አማኞች አላህን ይፈራሉ። ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ቀልባቸው በፍርሀት ይዋጣል። የዚህ አንቀፅም መልዕክት ይኸው ነው። በይበልጥ እናታችን አዒሻ የዚህን አንቀፅ መልዕክት ለመረዳት በማሰብ ነብያችንን (እነዚህ ሰዎች እየሰረቁ፤ እየዘሞቱ፤ ወለድ እየበሉ የአላህን ቅጣት የሚፈሩ ናቸው ማለት ነውን? በማለት ጠየቁ። ነብዩ ሲመልሱ «ፍፁም አይደለም እየሰገዱ፤ እየፆሙ ልባቸው በፍርሃት የተሞላ ማለት ነው» ብለው መለሱ።

إِنَّ ٱلَّذِينَ هُم مِّنْ خَشْيَةِ رَبِّهِم مُّشْفِقُونَ ﴿٥٧﴾ وَٱلَّذِينَ هُم بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمْ يُؤْمِنُونَ ﴿٥٨﴾ وَٱلَّذِينَ هُم بِرَبِّهِمْ لَا يُشْرِكُونَ ﴿٥٩﴾ وَٱلَّذِينَ يُؤْتُونَ مَآ ءَاتَوا۟ وَّقُلُوبُهُمْ وَجِلَةٌ أَنَّهُمْ إِلَىٰ رَبِّهِمْ رَٰجِعُونَ ﴿٦٠﴾ أُو۟لَٰٓئِكَ يُسَٰرِعُونَ فِى ٱلْخَيْرَٰتِ وَهُمْ لَهَا سَٰبِقُونَ ﴿٦١﴾

**57-61.** እነዚያ ጌታቸውን ከመፍራት የተነሳ ተጨናቂዎች የሆኑት፤ እነዚያም እነርሱ በጌታቸው ተአምራቶች የሚያምኑት፤ እነዚያም በጌታቸው ጣዖትን የማያጋሩት፤ እነዚያም የሚሰጡትን ነገር ሁሉ እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡ* ናቸው። እነዚያ በመልካም ስራዎች ይጣደፋሉ። እነርሱም ለርሷ ቀዳሚዎች ናቸው።

✷ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ስለዚህ የቁርኣን አንቀፅ ጠየኳቸው «እነዚያም የሚሰጡትን ነገር እነርሱ ወደ ጌታቸው ተመላሾች መሆናቸውን ልቦቻቸው የሚፈሩ ሆነው የሚሰጡት» እነዚህ ሰዎች ማለት አስካሪ መጠጦችን የሚጠጡና የሚሰርቁ ሰዎች ናቸውን?» የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) «የሲዲቅ ልጅ ሆይ! በፍፁም እነዚያ የሚፆሙት፤ የሚሰግዱት፤ ምፅዋት የሚሰጡትና የሚሰሩት ስራዎች በአላህ ዘንድ ተቀባይነት አያገኙም የሚሉ ናቸው። እንዲሁም እነዚያ በመልካም ነገር ላይ የሚነሳሱ ሰዎች ናቸው።»

وَلَا نُكَلِّفُ نَفْسًا إِلَّا وُسْعَهَاۚ وَلَدَيْنَا كِتَٰبٌ يَنطِقُ بِٱلْحَقِّ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿٦٢﴾ بَلْ
قُلُوبُهُمْ فِى غَمْرَةٍ مِّنْ هَٰذَا وَلَهُمْ أَعْمَٰلٌ مِّن دُونِ ذَٰلِكَ هُمْ لَهَا عَٰمِلُونَ ﴿٦٣﴾ حَتَّىٰٓ إِذَآ
أَخَذْنَا مُتْرَفِيهِم بِٱلْعَذَابِ إِذَا هُمْ يَجْـَٔرُونَ ﴿٦٤﴾ لَا تَجْـَٔرُوا۟ ٱلْيَوْمَۖ إِنَّكُم مِّنَّا لَا تُنصَرُونَ ﴿٦٥﴾

**62-65.** ማንኛይቱንም ነፍስ የችሎታዋን ያህል እንጂ አናስገድዳትም። እኛም ዘንድ በእውነት የሚናገር መጽሐፍ አለ። እነርሱም አይበደሉም። በእውነቱ ከሓዲያን ልቦቻቸው ከዚህ መጽሐፍ በዝንጋታ ውስጥ ናቸው። ለእነርሱም ከዚህ ሌላ እነርሱ ለእርሷ ሰሪዎችዋ የሆኑ መጥፎ ስራዎች አሏቸው። ቅምጥሎቻቸውንም በቅጣት በያዝናቸው ጊዜ ወዲያውኑ እነርሱ ይወተውታሉ። ዛሬ አትወትውቱ እናንተ ከእኛ ዘንድ አትረዱምና ይባላሉ።

قَدْ كَانَتْ ءَايَٰتِى تُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ فَكُنتُمْ عَلَىٰٓ أَعْقَٰبِكُمْ تَنكِصُونَ ﴿٦٦﴾ مُسْتَكْبِرِينَ بِهِۦ
سَٰمِرًا تَهْجُرُونَ ﴿٦٧﴾ أَفَلَمْ يَدَّبَّرُوا۟ ٱلْقَوْلَ أَمْ جَآءَهُم مَّا لَمْ يَأْتِ ءَابَآءَهُمُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿٦٨﴾
أَمْ لَمْ يَعْرِفُوا۟ رَسُولَهُمْ فَهُمْ لَهُۥ مُنكِرُونَ ﴿٦٩﴾

**66-69.** አንቀፆቼ በእናንተ ላይ በእርግጥ ይነበቡላችሁ ነበር። እናንተ ግን በተረከዞቻችሁ ላይ ወደ ኋላችሁ ትመለሱ ነበር። በእርሱ (በክልሉ ቤት) ኩሩዎች ሌሊት ተጫዋቾች (ቁርኣንንም) የምትተው ሆናችሁ (ትመለሱ ነበር ይባላሉ)። የቁርኣንን ንግግርን አያስተነትኑምን? ወይስ ለመጀመሪያዎቹ አባቶቻቸው ያልመጣ ነገር መጣባቸውን? ወይስ መልዕክተኛቸውን አላወቁምን? ስለዚህ እነርሱ በእርሱ ከሓዲያን ናቸውን?

ከአማኖች ምዕራፍ (67) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ቁረይሾች በካዕባ ዙሪያ እያመሹ ምንም ጠዋፍ ሳያደርጉ ይመለሱ ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

أَمْ يَقُولُونَ بِهِۦ جِنَّةٌۢۚ بَلْ جَآءَهُم بِٱلْحَقِّ وَأَكْثَرُهُمْ لِلْحَقِّ كَٰرِهُونَ ﴿٧٠﴾ وَلَوِ ٱتَّبَعَ ٱلْحَقُّ أَهْوَآءَهُمْ
لَفَسَدَتِ ٱلسَّمَٰوَٰتُ وَٱلْأَرْضُ وَمَن فِيهِنَّۚ بَلْ أَتَيْنَٰهُم بِذِكْرِهِمْ فَهُمْ عَن ذِكْرِهِم مُّعْرِضُونَ ﴿٧١﴾

**70-71.** ወይስ በእርሱ ዕብደት አለበት ይላሉን? እብድ አይደለም። እውነትን ይዞ መጣላቸው። አብዛኞቻቸውም ግን እውነትን ጠይዎች ናቸው። አላህ ዝንባሌዎቻቸውን በተከተለ ኖሮ ሰማያትና ምድር በውስጣቸውም ያለው ሁሉ በእርግጥ በተበላሸ ነበር። ይልቁንም ክብራቸው ያለበትን ቁርኣን አመጣንላቸው። እነርሱም ክብራቸውን ዘንጊዎች ናቸው።

**ከአማኞች ምዕራፍ ከአንቀፅ (63-71) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ**

1. አላዋቂነትና ጭፍን ደጋፊነት እውነትን ላለመቀበል ዋናው ምክኒያት መሆኑን፤
2. ቅጣተ በሚታይበተ ጊዜ የሚደረግ ተውበህ ፋይዳ እንደሌለው፤
3. የመካ ከሓዲያን የተቀጡበት ዋና ው ምክኒያት ቁርኣንን አለመስማታቸው መሆኑን እንረዳለን።

أَمْ تَسْـَٔلُهُمْ خَرْجًا فَخَرَاجُ رَبِّكَ خَيْرٌ ۖ وَهُوَ خَيْرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ﴿٧٢﴾

**72.** ወይስ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ግብርን ትጠይቃቸዋለህን? የጌታህ ችሮታ ከሁሉም በላጭ ነው። እርሱም ከሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነው።

وَإِنَّكَ لَتَدْعُوهُمْ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٧٣﴾ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْـَٔاخِرَةِ عَنِ ٱلصِّرَٰطِ
لَنَـٰكِبُونَ ﴿٧٤﴾ ۞ وَلَوْ رَحِمْنَـٰهُمْ وَكَشَفْنَا مَا بِهِم مِّن ضُرٍّ لَّلَجُّوا۟ فِى طُغْيَـٰنِهِمْ يَعْمَهُونَ ﴿٧٥﴾
وَلَقَدْ أَخَذْنَـٰهُم بِٱلْعَذَابِ فَمَا ٱسْتَكَانُوا۟ لِرَبِّهِمْ وَمَا يَتَضَرَّعُونَ ﴿٧٦﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا فَتَحْنَا عَلَيْهِم
بَابًا ذَا عَذَابٍ شَدِيدٍ إِذَا هُمْ فِيهِ مُبْلِسُونَ ﴿٧٧﴾

**73-77.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ ወደ ቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ትጠራቸዋለህ። እነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት ሰዎች ግን ከትክክለኛው መንገድ ዘንጊዎች ናቸው። ባዘንንላቸውና በእነርሱ ያለውን ጉዳትም ባነሳንላቸው ኖሮ በጥመታቸው ውስጥ የሚዋዥቁ ሆነው ይዘወትሩ ነበር። በእርግጥም በቅጣት ያዝናቸው። ታዲያ ለጌታቸው አልተናነሱም። እጅ የሚሰጡም አይደሉም። በእነርሱም ላይ የብርቱ ቅጣት ባለቤት የሆነ ደጃፍን በከፈትንባቸው ጊዜ ያን ጊዜ በእርሱ ተስፋ ቆራጮች ናቸው።

ከአማኞች ምዕራፍ ከ (75-76) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የመካ ሰዎች በጣም ሲያስቸግሩና ነብዩ (ﷺ) «ጌታዬ በነሱ ላይ የዩሱፍን የሰባት አመት አይነት ድርቅ በማውረድ እርዳኝ ብለው ዱዓ አድርገውባቸው ችግሩ ሲፈጠር አቡሱፍያን ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ በአላህና በዝምድና ይሁንብህ ቆዳ እየበላን ደም እየጠጣን ነው ሲላቸው ይህ አንቀፅ ወረደ። (ሱዩጢ) ሌሎች ደግሞ «ሱማማህ ኢብኑ ኡሳል ተማርኮ መጥቶ ከሰለመ በኋላ ወደ አገሩ ተመልሶ መኮችን ከገበያ ቦታቸው ሥለከለከላቸው አቡ ሱፍያን ወደ ነብዩ መጥቶ «በአላህ እና በዝምድና ይሁንብህ ለዓለም ራህመት ሁኚ ነው የመጣሁት ትል አልነበር» አላቸው «ታዲያስ» አሉት «አባቶችን በሰይፍ ልጆችን በረሀብ ፈጀሃቸው» በማለት ሲያማርራቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

وَهُوَ ٱلَّذِيٓ أَنشَأَ لَكُمُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَٱلۡأَفۡـِٔدَةَۚ قَلِيلٗا مَّا تَشۡكُرُونَ ﴿٧٨﴾
وَهُوَ ٱلَّذِي ذَرَأَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَإِلَيۡهِ تُحۡشَرُونَ ﴿٧٩﴾ وَهُوَ ٱلَّذِي يُحۡيِۦ وَيُمِيتُ
وَلَهُ ٱخۡتِلَٰفُ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴿٨٠﴾

**78-80.** እርሱ ያ መስሚያዎችን፣ ማያዎችንና ልቦችን ለእናንተ የፈጠረላችሁ ነው። ጥቂትን እንጂ አታመሰግኑም። እርሱም ያ በምድር ውስጥ የበተናችሁ ነው። በመጨረሻም ጊዜ ወደ እርሱም ትሰበሰባላችሁ። እርሱም ያ ህያው የሚያደርግ የሚገድልም ነው። የሌሊትና የቀን መተካካትም የእርሱ ነው። አታውቁምን?

بَلۡ قَالُواْ مِثۡلَ مَا قَالَ ٱلۡأَوَّلُونَ ﴿٨١﴾ قَالُوٓاْ أَءِذَا مِتۡنَا وَكُنَّا تُرَابٗا وَعِظَٰمًا أَءِنَّا لَمَبۡعُوثُونَ ﴿٨٢﴾
لَقَدۡ وُعِدۡنَا نَحۡنُ وَءَابَآؤُنَا هَٰذَا مِن قَبۡلُ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّآ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٨٣﴾

**81-83.** ይልቁንም የመካ ከሓዲያን ልክ የፊተኞቹ ህዝቦች እንዳሉት ብጤ አሉ። በሞትንና ዐፈርና አጥንቶች በሆንን ጊዜ እኛ እንደገና ተቀስቃሾች ነን? አሉ። ይህንን ሁኔታ እኛም ሆነ ከእኛ በፊት የነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረናል፤ ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም አሉ።

قُل لِّمَنِ ٱلۡأَرۡضُ وَمَن فِيهَآ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ﴿٨٤﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِۚ قُلۡ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٨٥﴾ قُلۡ
مَن رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ ٱلسَّبۡعِ وَرَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡعَظِيمِ ﴿٨٦﴾ سَيَقُولُونَ لِلَّهِۚ قُلۡ أَفَلَا تَتَّقُونَ ﴿٨٧﴾
قُلۡ مَنۢ بِيَدِهِۦ مَلَكُوتُ كُلِّ شَيۡءٖ وَهُوَ يُجِيرُ وَلَا يُجَارُ عَلَيۡهِ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ﴿٨٨﴾
سَيَقُولُونَ لِلَّهِۚ قُلۡ فَأَنَّىٰ تُسۡحَرُونَ ﴿٨٩﴾ بَلۡ أَتَيۡنَٰهُم بِٱلۡحَقِّ وَإِنَّهُمۡ لَكَٰذِبُونَ ﴿٩٠﴾

**84-90.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምድርና በውስጧ ያለው ሁሉ የማን ነው? የምታውቁ ከሆናችሁ እስቲ ንገሩኝ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርግጥ የአላህ ነው ይሉሃል። ታዲያ አትገሠፁምን? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሰባቱ ሰማያት ጌታ የታላቁ ዐርሽ ጌታ ማን ነው? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፤ እንግዲያ አትፈሩትምን? በላቸው። የነገሩ ሁሉ ግዛት በእጁ የሆነ እርሱ የሚጠብቅ በእርሱ ላይ የማይጠበቅ ማን ነው? የምታውቁ ከሆናችሁ እስቲ መልሱልኝ በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል፤ ታዲያ እንዴት ትታለላላችሁ? በላቸው። ይልቁንም እውነትን አመጣንላቸው እነርሱም ግን በመካዳቸው ውሸታሞች ናቸው።

مَا ٱتَّخَذَ ٱللَّهُ مِن وَلَدٍ وَمَا كَانَ مَعَهُۥ مِنْ إِلَٰهٍۚ إِذًا لَّذَهَبَ كُلُّ إِلَٰهِۭ بِمَا خَلَقَ وَلَعَلَا بَعْضُهُمْ عَلَىٰ بَعْضٍۚ سُبْحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٩١﴾ عَٰلِمِ ٱلْغَيْبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٩٢﴾

**91-92.** አላህ ምንም ልጅን አልያዘም (አልወለደም)፡፡ ከእርሱም ጋር አንድም ትክክለኛ አምላክ የለም፡፡ ያን ጊዜ (ሌላ አምላክ በነበረማ) አምላኩ ሁሉ የፈጠረውን ነገር በማስተዳደር ከሌላው በተለየ ነበር፡፡ ከፊላቸውም በከፊሉ ላይ በነገሰ ነበር፡፡ አላህ ከሓዲያን እሱን ከሚመጥኑበት (መግለጫ) ሁሉ ጠራ፡፡ ሩቁንና ቅርቡን ሁሉ ዐዋቂ ነው፡፡ በእርሱ ከሚያጋሩት ሁሉ ከፍ አለ፡፡

قُل رَّبِّ إِمَّا تُرِيَنِّي مَا يُوعَدُونَ ﴿٩٣﴾ رَبِّ فَلَا تَجْعَلْنِي فِي ٱلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٩٤﴾

**93-94.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ ሆይ! የሚስፈራሩበትን ቅጣት ብታሳየኝ፤ ጌታዬ ሆይ! በበደለኞች ህዝቦች ውስጥ አታድርገኝ በል፡፡

وَإِنَّا عَلَىٰٓ أَن نُّرِيَكَ مَا نَعِدُهُمْ لَقَٰدِرُونَ ﴿٩٥﴾ ٱدْفَعْ بِٱلَّتِي هِيَ أَحْسَنُ ٱلسَّيِّئَةَۚ نَحْنُ أَعْلَمُ بِمَا يَصِفُونَ ﴿٩٦﴾

**95-96.** እኛ የምናስፈራራቸውን ነገር ልናሳይህ በእርግጥ ቻዮች ነን፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዚያች መልካም በሆነችው ጠባይ መጥፎይቱን ነገር መልስ፡፡ እኛ ከሐዲያን የሚሉትን ሁሉ ዐዋቂዎች ነንና፡፡

وَقُل رَّبِّ أَعُوذُ بِكَ مِنْ هَمَزَٰتِ ٱلشَّيَٰطِينِ ﴿٩٧﴾ وَأَعُوذُ بِكَ رَبِّ أَن يَحْضُرُونِ ﴿٩٨﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَ أَحَدَهُمُ ٱلْمَوْتُ قَالَ رَبِّ ٱرْجِعُونِ ﴿٩٩﴾ لَعَلِّىٓ أَعْمَلُ صَٰلِحًا فِيمَا تَرَكْتُۚ كَلَّآۚ إِنَّهَا كَلِمَةٌ هُوَ قَآئِلُهَاۖ وَمِن وَرَآئِهِم بَرْزَخٌ إِلَىٰ يَوْمِ يُبْعَثُونَ ﴿١٠٠﴾

**97-100.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ ሆይ ከሰይጣናት ጉትጎታዎች ሁሉ በአንተ እጠበቃለሁ በል፡፡ ጌታዬ ሆይ! በአንተም ወደ እኔ (ከመጣዳቸው) ከመቅረባቸው እጠበቃለሁ በል፡፡ አንዳቸውን ሞት በመጣበት ጊዜ ጌታዬ ሆይ ወደ ምድረ ዓለም መልሱኝይላል፡፡ ችላ ብየ የተውኩትን በጎን ስራ ልሰራ እከጅላለሁና፡፡ (ይህን ከማለት) ይከልከል፡፡ እርስዋ እርሱ ተናጋሪዋ የሆነች ቃል ናት፡፡ ከበስተፊታቸውም እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ ግርዶ አለ፡፡

**ከአማኞች ምዕራፍ ከአንቀፅ (72-100) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሀላል ነገሮች መመገብ ግዴታ ስለመሆኑ፤
2. ኢስላም ለሁሉም የመጣ እምነት በመሆኑ ልንለያይበት እንደማይገባ፤
3. በዲን መጨቃጨቅ ብዙ ፈትናዎችን እንደሚያስከትል፤
4. ሰዎች የአላህን ዲን ትተው ሲሳይ ሲበዛላቸው አላህ ወዷቸው ሳይሆን እየፈተናቸው መሆኑን፤
5. አላህን መፍራት ምን ያህል ምንዳ እንዳለው፤
6. ለፈሪሃውያን ታላቅ ብስራት፤
7. በዲን ማስቸገር እንደሌለ፤
8. ድንቁርና (ጭፍንነት) እውነትን ላለመቀበል ዋናው ምክንያት ስለመሆኑ፤
9. ቅጣትን ባዩ ጊዜ የሚደረግ ተውባህ እንደማይጠቅም፤
10. ስሜትን የመከተል አደጋ ምን እንደሚመስል፤
11. ወደ አላህ የሚያደርሰው ቀጥተኛው መንገድ ኢስላም ስለመሆኑ፤
12. በትንሳኤ ቀን ማስተባበል ለመጥፎ ነገሮች ሁሉ መነሻ ስለመሆኑ፤
13. አላህ ለሰዎች ከዋለላቸው ፀጋዎች መካከል ዓይን፤ ጆሮ፤ ልብ መሆናቸውንና ማመስገን ተገቢ ስለ መሆኑ፤
14. ሙቶ የመነሳትን እውነታን ማረጋገጥ፤
15. ሐቅን አልቀበልም ያለን ሁሉ መውቀስ ተገቢ ስለመሆኑ፤
16. የአላህን ጌትነትና ብቸኛ አምላክነት፤
17. አላህን ከልጅና ከሚስት እንዲሁም ከአጋሮች የፀዳ ስለመሆኑ፤
18. ሐቅን ለማውጣትና ለማሳወቅ አዕምሮን መጠቀም ተገቢ ስለ መሆኑ
19. በኢስላም ዱዓ አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
20. መጥፎ ነገሮችንና የግፍ ተግባራትን በይቅርታ ማለፍ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
21. ከሰይጣን ተንኮል በአላህ መጠበቅ ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

فَإِذَا نُفِخَ فِي ٱلصُّورِ فَلَآ أَنسَابَ بَيۡنَهُمۡ يَوۡمَئِذٖ وَلَا يَتَسَآءَلُونَ ١٠١ فَمَن ثَقُلَتۡ مَوَٰزِينُهُۥ
فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٠٢ وَمَنۡ خَفَّتۡ مَوَٰزِينُهُۥ فَأُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ
فِي جَهَنَّمَ خَٰلِدُونَ ١٠٣ تَلۡفَحُ وُجُوهَهُمُ ٱلنَّارُ وَهُمۡ فِيهَا كَٰلِحُونَ ١٠٤ أَلَمۡ تَكُنۡ ءَايَٰتِي تُتۡلَىٰ
عَلَيۡكُمۡ فَكُنتُم بِهَا تُكَذِّبُونَ ١٠٥ قَالُواْ رَبَّنَا غَلَبَتۡ عَلَيۡنَا شِقۡوَتُنَا وَكُنَّا قَوۡمٗا ضَآلِّينَ ١٠٦
رَبَّنَآ أَخۡرِجۡنَا مِنۡهَا فَإِنۡ عُدۡنَا فَإِنَّا ظَٰلِمُونَ ١٠٧ قَالَ ٱخۡسَـُٔواْ فِيهَا وَلَا تُكَلِّمُونِ ١٠٨

**101-108.** በቀንዱም በተነፋ ጊዜ በዚያ ቀን በመካከላቸው ዝምድና የለምን አይጠያየቁምም። ሚዛኖቻቸው የከበዱላቸው ሰዎች እነዚያ እነርሱ ፍላጎታቸውን ያገኙ ናቸው። ሚዛኖቻቸውም የቀለሉባቸው ሰዎች እነዚያ እነርሱ ነፍሶቻቸውን ያከሰሩ ናቸው፤ በገሀነም ውስጥ ዘውታሪዎች ናቸው። ፊቶቻቸውን እሳት ትገርፋቸዋለች። እነርሱም በእርሷ ውስጥ ከንፈሮቻቸው

የተኮማተሩ ናቸው፡፡ አንቀፆቼ በእናንተ ላይ የሚነበቡላችሁና በእነርሱ የምታስተባብሉ አልነበራችሁምን? ይባላሉ፡፡ ታላቁ ጌታችን ሆይ፣ በእኛ ላይ መናጢነታችን አሸነፈችንና ጠማማ ህዝቦች ነበርን፡፡ ጌታችን ሆይ፣ ከእርሷ አውጣንና ወደ ዱንያ መልሰን፡፡ ከዚህ በኋላ ወደ ክህደት ብንመለስ እኛ በዳዮች ነን፡፡ ይላሉ አላህም ወራዶች ሆናችሁ በውስጧ አርፉችሁ ኑሩ እንጂ ፍፁም አታናግሩኝ ይላቸዋል፡፡

إِنَّهُۥ كَانَ فَرِيقٌ مِّنۡ عِبَادِي يَقُولُونَ رَبَّنَآ ءَامَنَّا فَٱغۡفِرۡ لَنَا وَٱرۡحَمۡنَا وَأَنتَ خَيۡرُ ٱلرَّٰحِمِينَ ١٠٩ فَٱتَّخَذۡتُمُوهُمۡ سِخۡرِيًّا حَتَّىٰٓ أَنسَوۡكُمۡ ذِكۡرِي وَكُنتُم مِّنۡهُمۡ تَضۡحَكُونَ ١١٠ إِنِّي جَزَيۡتُهُمُ ٱلۡيَوۡمَ بِمَا صَبَرُوٓاْ أَنَّهُمۡ هُمُ ٱلۡفَآئِزُونَ ١١١

**109-111.** እነሆ ከባሮቼ መካከል ጌታችን ሆይ፣ አምነናልና ማረን፡፡ እዘንልንም፡፡ አንተ ከአዛኞች ሁሉ ይበልጥ አዛኝ ነህ የሚሉ ክፍሎች ነበሩ፡፡ እኔን ማውሳትን እስከአስረሷችሁ ድረስም ማላገጫ አድርጋችሁ ያዛችኋቸው፡፡ በእነርሱም ላይ ትስቁባቸው ነበር፡፡ እኔ ዛሬ በትዕግስታቸው ምክንያት እነርሱ ፍላጎታቸውን የሚያገኙት እነርሱ ብቻ በመሆን መነዳኋቸው ይላቸዋል፡፡

قَٰلَ كَمۡ لَبِثۡتُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ عَدَدَ سِنِينَ ١١٢ قَالُواْ لَبِثۡنَا يَوۡمًا أَوۡ بَعۡضَ يَوۡمٖ فَسۡـَٔلِ ٱلۡعَآدِّينَ ١١٣ قَٰلَ إِن لَّبِثۡتُمۡ إِلَّا قَلِيلٗاۖ لَّوۡ أَنَّكُمۡ كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ١١٤

**112-114.** በምድር ውስጥ ስንትን አመታትን ቁጥር ቆያችሁ ይላቸዋል፡፡ አንድ ቀንን ወይም ከፊል ቀንን ቆየን፡፡ ቆጣሪዎችንም ጠይቅ ይላሉ፡፡ እናንተ የቆያችሁትን መጠን የምታውቁ ብትሆኑ ኖሮ (በእሳት ውስጥ ከምትቆዩት ጊዜ አንጻር) ጥቂትን ጊዜ እንጂ አልቆያችሁም ይላቸዋል፡፡

أَفَحَسِبۡتُمۡ أَنَّمَا خَلَقۡنَٰكُمۡ عَبَثٗا وَأَنَّكُمۡ إِلَيۡنَا لَا تُرۡجَعُونَ ١١٥ فَتَعَٰلَى ٱللَّهُ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡحَقُّۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ رَبُّ ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡكَرِيمِ ١١٦

**115-116.** (ሰዎች ሆይ!) የፈጠርናችሁ ለከንቱ መሆኑን እናንተም ወደ እኛ የማትመለሱ መሆናችሁን ጠረጠራችሁን? የእውነቱ ንጉስ አላህ ከፍተኛነት ተገባው፡፡ ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ አምላክ የለም፡፡ የዚያ የሚያምረው ዐርሽ ጌታም እሱ ብቻ ነው፡፡

وَمَن يَدْعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ لَا بُرْهَٰنَ لَهُۥ بِهِۦ فَإِنَّمَا حِسَابُهُۥ عِندَ رَبِّهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُفْلِحُ ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿١١٧﴾

**117.** ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ ለእርሱ በእርሱ ማስረጃ የሌለውን የሚገዛ ሰው ሁሉ ምርመራው እጌታው ዘንድ ብቻ ነው። እነሆ ከሓዲያን አይድኑም።

وَقُل رَّبِّ ٱغْفِرْ وَٱرْحَمْ وَأَنتَ خَيْرُ ٱلرَّٰحِمِينَ ﴿١١٨﴾

**118.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ ሆይ፣ ማር። እዘንም። አንተም ከአዛኞች ሁሉ በላጭ ነህና፡ በል፡

**ከአማኞች ምዕራፍ ከአንቀፅ (101-118) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
2. የትንሳኤ ቀን ስራዎች እንደሚመዘኑ፤
3. ኢስራፌል በቀንድ እንደሚነፋ፤
4. ሰዎች ቀደርን ምክንያት ሊያደርጉ እንደማይገባ፤
5. የእሳት ሰዎች ፀፀት ምን እንደሚመስል፤
6. ወደ አላህ መተናነስና በመልካም ስራ ወደ አላህ መቃረብ ተገቢ ስለመሆኑ፤
7. በሙስሊም ላይ ማፌዝም ሆነ ማላገጥ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
8. የቂያማ ቀን መከራና ስቃይ ከባድ እንደሆነ፤
9. አላህ ከጨዋታና ከመቀለድ የፀዳ ስለመሆኑ፤
10. ከአላህ ሌላ ያለን ነገር የሚጣራ አጋሪ እንደሆነ፤
11. ከሓዲያን ከሳሪዎች እንደሆኑ፤
12. ለሙዕሚኖች ዱዓ ማድረግ ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የአማኞች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (24)
# የብርሃን ምዕራፍ
## (ሱረቱ አንኑር)

سُورَةُ النُّورِ

### የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (64) ናቸው።

### የሱረቱ አን-ኑር መግቢያ

የብርሃን ምዕራፍ ስልሳ አራት አንቀፅ ይዞ በመዲና የወረደ ምዕራፍ ነው። ማህበረሰቡን ከዝሙት ማፅዳትና መጥፎ ነገርን በሙስሊሞች ዘንድ በተግባርም ሆነ በአንደበት የማዛባትና የማስፋፋትን ተግባር መግታት ግዴታ ስለመሆኑ ያስተምራል። ለዚህም ጥፋት ቅጣት እንደተደነገገና የባለትዳር ዝሙተኝነት በተመለከተ ልዩ ህግ እንደተደነገገ ያብራራል። በዝሙት ስራ ላይ የሚደረጉ ውሸቶችን ያወግዛል። ሙስሊም የሆነ ሰው መጥፎ ወሬዎችን ሲወሩለት ማስረጃ እንደሚያስፈልጋቸው አውቆ መጠየቅና ማጣራት እንዳለበት፤ ይህ አይነቱን ወሬ ማጣራት ያልቻለና ተቀብሎ ያናፈሰ ከዋሾዎች አንዱ መሆኑንና የሚወሰድበትም እርምጃ ከፍተኛ መሆኑን ያስተምራል። በመቀጠልም ስለ ሴቶች አለባበስና ቤተሰባዊ ስርአት ሰፊ አስተምህሮት ይሰጣል። በአጠቃላይ ብዙ ህግጋቶችን ያካተተ ሲሆን በወንድና በሴት መካከል ነገሮች በተመለከተ፤

ንፁህን ሴቶችን የሚሰድቡ ሰዎች ቅጣት፤

የመረጋገምን ህግ፤ የእሜት ዓኢሻን ንፁህነት፤

በሴትም ሆነ በወንድ አማኝ ላይ መጥፎ ነገሮችን ከመስራት መከልከል፤

የበደለን ሰው በይቅርታ ማለፍን በተመለከተ፤

ወደ ሰዎች ቤት ሲገባ ፈቃድ መጠየቅ አስፈላጊ መሆኑን፤

ስለ ሰላም ስርዓትና አስፈላጊነት፤

በስራችን የሚኖሩትን ባሮቻችንም ትዳር ማስያዝ ተገቢ ስለመሆኑ፤

ከሰይጣን መንገድ መራቅ እንደሚገባ ያስተምራል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

سُورَةٌ أَنزَلۡنَٰهَا وَفَرَضۡنَٰهَا وَأَنزَلۡنَا فِيهَآ ءَايَٰتِۭ بَيِّنَٰتٍ لَّعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ١

**1.** (ሙስሊሞች ሆይ!) (ይህ) ያወረድነውና በእናንተ ላይ (እንድትሰሩበት) የደነገግነው ምእራፍ ነው። በርሷም ውስጥ ትገሰፁ ዘንድ ግልጾችን አንቀፆችን አውርደናል።

ٱلزَّانِيَةُ وَٱلزَّانِي فَٱجۡلِدُواْ كُلَّ وَٰحِدٖ مِّنۡهُمَا مِاْئَةَ جَلۡدَةٖۖ وَلَا تَأۡخُذۡكُم بِهِمَا رَأۡفَةٞ فِي دِينِ ٱللَّهِ إِن كُنتُمۡ تُؤۡمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۖ وَلۡيَشۡهَدۡ عَذَابَهُمَا طَآئِفَةٞ مِّنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٢ ٱلزَّانِي لَا يَنكِحُ إِلَّا زَانِيَةً أَوۡ مُشۡرِكَةٗ وَٱلزَّانِيَةُ لَا يَنكِحُهَآ إِلَّا زَانٍ أَوۡ مُشۡرِكٞۚ وَحُرِّمَ ذَٰلِكَ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٣

**2-3.** [*1]ዝሙተኛይቱ ሴትና ዝሙተኛው ወንድ ከሁለቱ እያንዳንዳቸው (ያላገቡ እንደሆኑ) መቶ ግርፋትን ግረፏቸው። በእነርሱ ላይ በደነገገው በአላህ ፍርድ ርህራሄ አትያዛችሁ። በአላህና በመጨረሻው ቀን የምታምኑ እንደሆናችሁ (ለእነርሱ አትራሩ)። (ሙስሊሞች ሆይ!) ቅጣታቸውንም በምትፈፅሙበት ጊዜ ከምዕመናን የተወሰኑ ቡድኖች ይገኙበት። ዝሙተኛ ወንድ ዝሙተኛን ሴት ወይም በአላህ አጋሪን ሴት እንጂ ሌላን አያገባም (አይፈልግም)። ዝሙተኛይቱም ሴት ዝሙተኛ ወይም በአላህ አጋሪ ወንድ እንጂ ሌላ አያገባትም (አይፈልጋትም)።[*2] ይህም በምዕመናን ላይ ተከልክሏል።

*1 ይህ ህግ ያላገቡና ባርነት የሌላቸው ሰዎች ቅጣት ነው። ያገቡ ሰዎች ቅጣት ግን ተቀጥቅጦ መገደል እንደሆነ በትክክለኛ ሐዲስ ተደንግጓል። በተጨማሪም ይህ አንቀፅ በሴቶች (15) ኛና (16) ኛው አናቅፅ ላይ ተደንግጎ የነበረውን የእስራትና የማሰቃየት ህግ ሽሯል። ይህ ህግ ያላገቡና ባርነት የሌላቸው ሰዎች ቅጣት ነው። ያገቡ ሰዎች ዝሙት ሲፈጽሙ የሚወሰንባቸው ቅጣት ግን ተቀጥቅጦ መገደል እንደሆነ በትክክለኛ ሐዲስ ተደንግጓል። በተጨማሪም ይህ አንቀፅ በሴቶች ምዕራፍ (15) ኛና (16) ኛው አናቅፅ ላይ ተደንግጎ የነበረውን የእስራትና የማሰቃየት ህግ ሽሯል።

(ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዲህ ብለዋል፡- «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጋብቻ ሳይኖረው ዝሙት የፈፀመ ሰውን ለአንድ አመት ያህል ከሀገር እንዲሰደድና ሕጋዊ ቅጣቱን እንዲቀበል ፈርደውበታል» ሕጋዊ ቅጣትን ማለት ጋብቻ ሳይኖረው ዝሙት በመፈፀሙ አላህ የደነገገበትን አንድ መቶ ጅራፍ እንዲገረፍ የፍርድ ውሳኔ አስተላለፈበት ማለት ነው።

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ጃቢር ኢብኑ ዐብደላህ እንዳስተላለፉት፡- የበኒ አስለም ጎሳ የሆነ ሰው ወደ አላህ አላህ መልዕክተኛ መጣና ከጋብቻ ውጪ ዝሙት መፈፀሙን ነገራቸውና በራሱ ላይ አራት ምስክሮችን አስመሰከረ። ይህን ጊዜ የአላህ መልዕክተኛ ግለሰቡ በድንጋይ ተቀጥቅጦ እንዲገደል አዘዙ። በድጋይ ተቀጥቅጦም ሞተ።

✴2 ይህ አባባል በተፍሲር ምሁራን ዘንድ በሁለት ተፈቷል። አንዳንዶች «ጋብቻ ማለት ነው» ሲሉ ሌሎች ደግሞ «ግንኙነት ማለት ነው» ብለዋል። የሚሻለው ግን ሁለተኛው አባባል ነው። ምክንያቱም ዝሙተኛ ሙስሊምም ቢሆን በአላህ የምታጋራን ሴት ሊያገባ አይችልምና። ስለዚህ ዝሙት ለማድረግ የሚሳሳተው በዝሙተኛና በአጋሪ ላይ ብቻ መሆኑን ያመለክታል።

ይህ አንቀፅ ላይ ላዩን ሲመለከቱት ዝሙተኛ ሰው ማንንም ማግባት እንደማይችል ያመለክታል። ኢስላም ማንኛውንም ዓይነት በሴቶች ላይ የሚደርሱ ትንኮሳዎችን አጥብቆ ያወግዛል። ማውገዝም ብቻ ሳይሆን በአጥፊዎቹ ላይ ቅጣትን አስቀምጧል። ሴቶች ላይ ከሚደርሱ ትንኮሳዎች ውስጥ በአንዳንዶች እንደ ቀላል የሚታየውም ስም ማጥፋትን አስመልክቶ አላህ በቁርአኑ ይህን «እነዚያ ጥብቆችን ሴቶችን (በዝሙት) የሚሰድቡ ከዚያም አራት ምስክሮችን ያላመጡ» (አንኑር፡4) በዚሁ ላይ «እነዚያ ጥብቆችን ከዝሙት ዘንጊዎቹን (ዝሙት ያልፈፀሙትን) ምዕመናትን የሚሰድቡ፤ በቅርቢቱም በመጨረሻይቱም ዓለም ተረገሙ። ለነርሱ ታላቅ ቅጣት አላቸው» (አንኑር፡23) ያለውን አውርዷል። ሴትን መስደብ በተለይ እናትን ዛሬ ዛሬ በየመንደሩ እንደተራና ቀላል ነገር ተቆጥሮ «እናትህ እንዲህ ትሁን» አይነት ስድቦችን መስማቱ ቀላል ነገር ሆኗል። ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) ወላጅን መስደብ ከታላላቅ ወንጀሎች እንደሚቆጠር እንዲህ በማለት አስተምረዋል። «አንድ ሰው ወላጆቹን መስደቡ ከታላላቅ ወንጀሎች ነው» በማለት ተናገሩ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሰው ወላጆቹን ይሰድባልን? አላቸው። «አዎ! እርሱ የሌላውን ሰው አባት ይሰድባል ያሰው ደግሞ አባቱን ይሰድብበታል። የሌላ ሰው እናት ይሰድባል ያሰው ደግሞ እናቱን ይሰድብበታል» አሉ።

ከብርሃን ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩ (ﷺ) ጊዜ የነበሩ ዝሙተኛ ሴቶችን ለማግባት አንዳንድ ሰዎች ወደ ነብዩ (ﷺ) እየመጡ ጥያቄ ሲያቀርቡ ክልክል መሆኑን ለማስተማር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

وَٱلَّذِينَ يَرۡمُونَ ٱلۡمُحۡصَنَٰتِ ثُمَّ لَمۡ يَأۡتُواْ بِأَرۡبَعَةِ شُهَدَآءَ فَٱجۡلِدُوهُمۡ ثَمَٰنِينَ جَلۡدَةً وَلَا تَقۡبَلُواْ لَهُمۡ شَهَٰدَةً أَبَدٗاۚ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡفَٰسِقُونَ ﴿٤﴾ إِلَّا ٱلَّذِينَ تَابُواْ مِنۢ بَعۡدِ ذَٰلِكَ وَأَصۡلَحُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ﴿٥﴾

**4-5.** እነዚያ ጥብቆችን ሴቶች በዝሙት የሚሰድቡ ከዚያ በሰደቡበት አራት ምስክሮች ያላመጡ ሰማንያ ግርፋት ግረፏቸው።✴ ከእነርሱም ምስክርነትን ለሁልጊዜ አትቀበሉ። እነዚያም አመፀኞች ናቸው። እነዚያ ከዚህ በኋላ የተፀፀቱና ሥራቸውን ያሳመሩ ሲቀሩ። አላህ በጣም መሓሪና አዛኝ ነውና።

✴ ይህ ቅጣት ግርፋት ነው ወይስ እስራት በሚል ልዩነቶች ተንፀባርቀዋል። የተሻለው ግርፋት ነው የሚለውን ነው።

ከብርሃን ምዕራፍ (4) ኛው እና (5) ኛው አንቀፅ የወረዱበት ምክንያት፡- በዓኢሻ ጉዳይ ላይ ገብተው ስማቸውን ባጠፉ ሰዎች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

وَٱلَّذِينَ يَرۡمُونَ أَزۡوَٰجَهُمۡ وَلَمۡ يَكُن لَّهُمۡ شُهَدَآءُ إِلَّآ أَنفُسُهُمۡ فَشَهَٰدَةُ أَحَدِهِمۡ أَرۡبَعُ شَهَٰدَٰتِۭ
بِٱللَّهِ إِنَّهُۥ لَمِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ٦ وَٱلۡخَٰمِسَةُ أَنَّ لَعۡنَتَ ٱللَّهِ عَلَيۡهِ إِن كَانَ مِنَ ٱلۡكَٰذِبِينَ ٧
وَيَدۡرَؤُاْ عَنۡهَا ٱلۡعَذَابَ أَن تَشۡهَدَ أَرۡبَعَ شَهَٰدَٰتِۭ بِٱللَّهِ إِنَّهُۥ لَمِنَ ٱلۡكَٰذِبِينَ ٨ وَٱلۡخَٰمِسَةَ
أَنَّ غَضَبَ ٱللَّهِ عَلَيۡهَآ إِن كَانَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ٩ وَلَوۡلَا فَضۡلُ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡ وَرَحۡمَتُهُۥ وَأَنَّ
ٱللَّهَ تَوَّابٌ حَكِيمٌ ١٠

**6-10.** እነዚያ ሚስቶቻቻውን (በዝሙት) የሚሰድቡ ለነሱም ከነፍሶቻቸው በስተቀር ምስክሮች የሌሏቸው የሆኑ የአንዳቸው ምስክርነት እነርሱ ከእውነተኞች ለመሆናቸው በአላህ ስም አራት ጊዜ ምሎ መመስከር ነው፡፡ አምስተኛይቱም ከውሸታሞች ቢሆን በእርሱ ላይ የአላህ እርግማን ይኑርበት (ብሎ መመስከር) ነው፡፡ እርሱም ከውሸታሞች ነው ብላ አራት ጊዜ መመስከሮችን በአላህ ስም መመስከርዋ ከእርሷ ላይ ቅጣትን ይከላከልላታል፡፡ አምስተኛይቱም እርሱ ከእውነተኞች ቢሆን በርስዋ ላይ የአላህ ቁጣ ይኑርባት ብላ መመስከርዋ ነው፡፡ (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በእናንተ ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረና አላህ ፀፀትን ተቀባይና ጥበበኛ ባልሆነ ኖሮ (ውሸታሙን ሁሉ በዚሁ ዐለም ላይ ይገልፀው ነበር)፡፡

ከብርሃን ምዕራፍ ከ (6-10) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሚስቱን በዝሙት ጠርጥሯት በነበረው በሒላል ኢብኑ ኡመያህ ምክንያት ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት፡፡

**ከብርሃን ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-10) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ትዳር ያልጀመሩ ሰዎች ዝሙት ሲሰሩ ቅጣታቸው መቶ ጅራፍ መገረፍ ብቻ መሆኑን፤
2. ይህ ግርፋት መፈፀም ያለበት ደግሞ በተወሰኑ ሰዎች ምስክሮች ፊት እንደሆነ፤
3. ዝሙተኛን ሰው ካልቶበተ በስተቀር ማግባት እንደማይፈቀድ፤
4. የቀዝፍ (መቅጫ) (80) የጅራፍ ግርፋት መሆኑን፤
5. ቀዝፍ ያደረገ ሰው ንስሀ ካልገባ በስተቀር ለምስክርነት እንደማይበቃ፤
6. የትኛውም ወንጀለኛ በትክክል ንስሀ ከገባ ተቀባይነት እንደለ፤
7. አራት ምስክሮችን ሳይዝ ሚስቱን ቀዝፍ ማድረግ እንደማይገባ፤
8. ከኢስላም ህግጋት አንዱ የሆነው የሊዓንን ስርዓት እንማራለን፡፡

إِنَّ ٱلَّذِينَ جَآءُو بِٱلۡإِفۡكِ عُصۡبَةٞ مِّنكُمۡۚ لَا تَحۡسَبُوهُ شَرّٗا لَّكُمۖ بَلۡ هُوَ خَيۡرٞ لَّكُمۡۚ
لِكُلِّ ٱمۡرِيٕٖ مِّنۡهُم مَّا ٱكۡتَسَبَ مِنَ ٱلۡإِثۡمِۚ وَٱلَّذِي تَوَلَّىٰ كِبۡرَهُۥ مِنۡهُمۡ لَهُۥ عَذَابٌ عَظِيمٞ ١١
لَّوۡلَآ إِذۡ سَمِعۡتُمُوهُ ظَنَّ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتُ بِأَنفُسِهِمۡ خَيۡرٗا وَقَالُواْ هَٰذَآ إِفۡكٞ مُّبِينٞ ١٢

لَّوْلَا جَآءُو عَلَيْهِ بِأَرْبَعَةِ شُهَدَآءَۚ فَإِذْ لَمْ يَأْتُواْ بِٱلشُّهَدَآءِ فَأُوْلَٰٓئِكَ عِندَ ٱللَّهِ هُمُ
ٱلْكَٰذِبُونَ ﴿١٣﴾ وَلَوْلَا فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُۥ فِى ٱلدُّنْيَا وَٱلْءَاخِرَةِ لَمَسَّكُمْ فِى مَآ
أَفَضْتُمْ فِيهِ عَذَابٌ عَظِيمٌ ﴿١٤﴾ إِذْ تَلَقَّوْنَهُۥ بِأَلْسِنَتِكُمْ وَتَقُولُونَ بِأَفْوَاهِكُم مَّا لَيْسَ
لَكُم بِهِۦ عِلْمٌ وَتَحْسَبُونَهُۥ هَيِّنًا وَهُوَ عِندَ ٱللَّهِ عَظِيمٌ ﴿١٥﴾ وَلَوْلَآ إِذْ سَمِعْتُمُوهُ قُلْتُم مَّا
يَكُونُ لَنَآ أَن نَّتَكَلَّمَ بِهَٰذَا سُبْحَٰنَكَ هَٰذَا بُهْتَٰنٌ عَظِيمٌ ﴿١٦﴾ يَعِظُكُمُ ٱللَّهُ أَن تَعُودُواْ
لِمِثْلِهِۦٓ أَبَدًا إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿١٧﴾ وَيُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمُ ٱلْءَايَٰتِۚ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٌ ﴿١٨﴾

**11-18.** እነዚያ መጥፎን ውሸት ያመጡ ከናንተው የሆኑ ጭፍሮች ናቸው፡፡ ለእናንተ ክፉ ነገር ነው ብላችሁ አታስቡት በእውነቱ እርሱ ለእናንተ መልካም ነገር ነው፡፡ ከእነርሱ (ከጭፍሮቹ) ለእያንዳንዱ ሰው ከኃጢአት የሠራው ሥራ ዋጋ አለው፡፡ ያም ከእነርሱ ትልቁን ኃጢአት የተሸከመው ለእርሱ ከባድ ቅጣት አለው፡፡ (ውሸቱን) በሰማችሁት ጊዜ ምዕመናንና ምዕመናት በነፍሶቻቸው ለምን ደግን ነገር አልጠረጠሩም? ለምንስ ይህ ግልጽ ውሸት ነው አላሉም? በእርሱ ላይ ለምን አራትን ምስክሮች አላመጡም? ምስክሮቹንም ካላመጡ እነዚያ አላህ ዘንድ ውሸታሞቹ እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም በእናንተ ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ በውስጡ በገባችሁበት ወሬ ምክንያት ታላቅ ቅጣት በእርግጥ በደረሰባችሁ ነበር፡፡ በምላሶቻችሁም በምትቀባበሉት ጊዜ ለእናንተም በእርሱ እውቀት በሌላችሁ ነገር በአፎቻችሁ በተናገራችሁና እርሱ አላህ ዘንድ ከባድ ኃጢአት ሆኖ ሳለ ቀላል አድርጋችሁ ባሰባችሁት ጊዜ ከባድ ቅጣት በነካችሁ ነበር፡፡ በሰማችሁት ጊዜ በዚህ ጉዳይ ልንናገር ለእኛ አይገባንም፡፡ አላህ ጥራት ይገባህ፡፡ ይህ ከባድ ቅጥፈት ነው አትሉም ነበርን? ምዕመናን እንደሆናችሁ ወደ ዚህ መሰል ተግባር ብጤው በፍፁም እንዳትመለሱ፡፡ አላህ ይገስጻችኋል፡፡ ለእናንተም አላህ አንቀፆችን ይገልጽላችኋል፡፡ አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነው፡፡

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحِبُّونَ أَن تَشِيعَ ٱلْفَٰحِشَةُ فِى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ فِى ٱلدُّنْيَا
وَٱلْءَاخِرَةِۚ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ وَأَنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ﴿١٩﴾ وَلَوْلَا فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ
وَرَحْمَتُهُۥ وَأَنَّ ٱللَّهَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴿٢٠﴾

**19-20.** እነዚያ በእነዚያ በአላህ ባመኑት ሰዎች ውስጥ መጥፎ ወሬ እንድትስፋፋ የሚወዱ ለእነርሱ በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም አሳማሚ ቅጣት አላቸው።* አላህ ሁሉን ነገር ያውቃል እናንተ ግን አታውቁም። በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታውና እዝነቱ ባልነበረ አላህም ሩህሩህና አዛኝ ባልሆነ ኖሮ (ቶሎ ባጠፋችሁ ነበር)።

* ዓኢሻ በመልኳም ሆነ በውበቷ ከነብዩ (ﷺ) ሚስቶች መካከል ትወዳደረኝ የነበረችው ዘይነብ ቢንት ጀህሽን በእኔ ጉዳይ ጠይቀዋት «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጆሮዬንም አይኔንም እጠብቃለሁ። ስለሷ ኸይር እንጂ ምንም የማውቀው ነገር የለኝ» አለች። እህቷ ሽምነት ቢንት ጀህሽ «ስለ እሷ እከራከራለሁ» ብላ ከጠፉ ሰዎች ሆነች። ዘይነብ ግን የአላህ ፍረቻዋ ጠበቃት ብለዋል።

۞ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تَتَّبِعُوا۟ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيْطَـٰنِ ۚ وَمَن يَتَّبِعْ خُطُوَٰتِ ٱلشَّيْطَـٰنِ فَإِنَّهُۥ يَأْمُرُ بِٱلْفَحْشَآءِ وَٱلْمُنكَرِ ۚ وَلَوْلَا فَضْلُ ٱللَّهِ عَلَيْكُمْ وَرَحْمَتُهُۥ مَا زَكَىٰ مِنكُم مِّنْ أَحَدٍ أَبَدًا وَلَـٰكِنَّ ٱللَّهَ يُزَكِّى مَن يَشَآءُ ۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٌ ﴿٢١﴾

**21.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! የሰይጣንን እርምጃዎች አትከተሉ። የሰይጣንን እርምጃዎች የሚከተል ሰው ሁሉ ኃጢአትን ተሸከመ። እርሱ በመጥፎና በሚጠላ ነገር ያዛልና፤ በእናንተም ላይ የአላህ ችሮታና እዝነቱ ባልነበረ ኖሮ ከናንተ አንድም ፈጽሞ (ከወንጀል) ባልጠራ ነበር። ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያጠራል። አላህ ለሚባለው ነገር ሁሉ ሰሚ ለሚፈፀመው ነገር ሁሉ አዋቂ ነው።

وَلَا يَأْتَلِ أُو۟لُوا۟ ٱلْفَضْلِ مِنكُمْ وَٱلسَّعَةِ أَن يُؤْتُوٓا۟ أُو۟لِى ٱلْقُرْبَىٰ وَٱلْمَسَـٰكِينَ وَٱلْمُهَـٰجِرِينَ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ۖ وَلْيَعْفُوا۟ وَلْيَصْفَحُوٓا۟ ۗ أَلَا تُحِبُّونَ أَن يَغْفِرَ ٱللَّهُ لَكُمْ ۗ وَٱللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٢٢﴾

**22.** ከናንተም መካከል የችሮታና የክብረት ባለቤቶች የሆኑት ከፍሎች ለቅርብ ዘመዶችና ለድሆችና በአላህም መንገድ ለተሰደዱ ሰዎች ምንንም ነገር ላይሰጡ አይማሉ። ይቅርታም ያድርጉ። ጥፋተኞቹን ይለፉም። አላህ ለእናንተ ሊምር አትወዱምን? አላህ መሓሪና አዛኝ ነው።

ከብርሃን ምዕራፍ (22) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡ በክር ሲዲቅ ሚስጠሕ ለተባለ የአክስታቸው ልጅ በዓኢሻ ጉዳይ ከገባ አልረዳውም ብለው ስለማሉ ነበር ይህ አንቀፅ ወርዶ ከዚህ መሀላቸው እንዲመለሱ የመከራቸው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَرۡمُونَ ٱلۡمُحۡصَنَٰتِ ٱلۡغَٰفِلَٰتِ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ لُعِنُواْ فِي ٱلدُّنۡيَا وَٱلۡأٓخِرَةِ وَلَهُمۡ عَذَابٌ
عَظِيمٞ ٢٣ يَوۡمَ تَشۡهَدُ عَلَيۡهِمۡ أَلۡسِنَتُهُمۡ وَأَيۡدِيهِمۡ وَأَرۡجُلُهُم بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٢٤ يَوۡمَئِذٖ
يُوَفِّيهِمُ ٱللَّهُ دِينَهُمُ ٱلۡحَقَّ وَيَعۡلَمُونَ أَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡحَقُّ ٱلۡمُبِينُ ٢٥

**23-25.** እነዚያ ጥብቆቹንና ከዝሙት ዘንጊዎቹን ምዕምናት የሚሰድቡ ሰዎች ሁሉ በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ተረገሙ። ለእነርሱም ታላቅ ቅጣት አለባቸው። በእነርሱ ላይ ምላሶቻቸው እጆቻቸውና እግሮቻቸው ይሰሩት በነበሩት ነገር ሁሉ በሚመሰክሩባቸው ቀን ከባድ ቅጣት አለላቸው። በዚያም ቀን አላህ ተገቢ ዋጋቸውን ይሞላላቸዋል። አላህም እርሱ መኖሩ የተረጋገጠ ሁሉን ነገር ገላጭ መሆኑን ያውቃሉ።

ٱلۡخَبِيثَٰتُ لِلۡخَبِيثِينَ وَٱلۡخَبِيثُونَ لِلۡخَبِيثَٰتِۖ وَٱلطَّيِّبَٰتُ لِلطَّيِّبِينَ وَٱلطَّيِّبُونَ لِلطَّيِّبَٰتِۚ
أُوْلَٰٓئِكَ مُبَرَّءُونَ مِمَّا يَقُولُونَۖ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَرِزۡقٞ كَرِيمٞ ٢٦

**26.** መጥፎዎቹ ሴቶች ለመጥፎዎቹ ወንዶች፣ መጥፎዎቹ ወንዶችም ለመጥፎዎቹ ሴቶች ብቻ የተገቡ ናቸው። ጥሩዎቹ ሴቶችም ለጥሩዎቹ ወንዶች፤ ጥሩዎቹ ወንዶችም ለጥሩዎቹ ሴቶች ብቻ የሚገቡ ናቸው። እነዚያ መጥፎዎቹ ሰዎች ከሚሉት ነገር ንፁህ የተደረጉ ናቸው። ለእነርሱ በጀነት ምህረትና መልካም ሲሳይ አለላቸው።

**ከብርሃን ምዕራፍ ከአንቀፅ (11-26) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህ ውሳኔ ሁሉም መልካም መሆኑን፤
2. በኢስላም ቅጣት የሚወሰነው በወንጀሉ ልክ መሆኑን፤
3. ማንኛውም አማኝ አንድን አማኝ በዝሙት የጠረጠረና የሰደበ ሰው ሲመጣለት «አራት ምስክሮችን ማምጣት ትችላለህን?» ብሎ መጠየቅ ሲሆን ማምጣት ካልቻለ ውሸታም ነህ ማለት እንዳለኢብኑ፤
4. አላህ ንጹሕ ሰው በሐሰት በዝሙት እንዳይወመጀል ለመከላከል ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች ማስቀመጡን፤
5. ሰይጣንን ከመከተል መቆጠብ፤
6. አላህ ሰይጣንን ከመከተል የጠበቃቸው ሰዎች መኩራት እንዳለባቸው፤
7. አንድን ነገር ለመስራትም ሆነ ላለመስራት ተቃራኒው የተሻለ መሆኑን አይቶ መስራት እንደሚገባ፤
8. የተከበሩ ሰዎች አጥፍተው ከቶበቱ ይቅርታ ማለት እንዳለብን፤
9. ንፁህንን ሴቶችን መስደብ ከፍተኛ ወንጀል ስለመሆኑ፤
10. ሙቶ መነሳት ያለ መሆኑንና ምርመራ ያለ ስለመሆኑ፤
11. መጥፎ ለመጥፎ ደግ ለደግ ተመጣጣኝ መሆኑን፤
12. ከዓኢሻና ከሳቸው ጋር የታሙት ሶህቢ ከታሙበት ወንጀል ንፁህ መሆናቸውን፤
13. ዓኢሻና ከሳቸው ጋር የታሙት ሶሃቢ በጀነት መበሰራቸውን እንማራለን።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَدۡخُلُواْ بُيُوتًا غَيۡرَ بُيُوتِكُمۡ حَتَّىٰ تَسۡتَأۡنِسُواْ وَتُسَلِّمُواْ عَلَىٰٓ أَهۡلِهَاۚ
ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تَذَكَّرُونَ ﴿٢٧﴾ فَإِن لَّمۡ تَجِدُواْ فِيهَآ أَحَدٗا فَلَا تَدۡخُلُوهَا حَتَّىٰ
يُؤۡذَنَ لَكُمۡۖ وَإِن قِيلَ لَكُمُ ٱرۡجِعُواْ فَٱرۡجِعُواْۖ هُوَ أَزۡكَىٰ لَكُمۡۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ عَلِيمٞ ﴿٢٨﴾
لَّيۡسَ عَلَيۡكُمۡ جُنَاحٌ أَن تَدۡخُلُواْ بُيُوتًا غَيۡرَ مَسۡكُونَةٖ فِيهَا مَتَٰعٞ لَّكُمۡۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ مَا
تُبۡدُونَ وَمَا تَكۡتُمُونَ ﴿٢٩﴾

**27-29.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! እስከምታስፈቅዱና በባለቤቶቹ ላይ ሰላምታን እስከምታቀርቡ ድረስ በሌላ ሰዎች ቤቶች አትግቡ። ይህ ጉዳይ ለእናንተም መልካም ነው። እናንተ ትገነዘቡ ዘንድ በዚህ ታዘዛችሁ። በውስጧም አንድንም ሰው ባታገኙ ለእናንተ እስከሚፈቀድላችሁ ድረስ አትግቧት። ለእናንተ ተመለሱ ከተባላችሁ ተመለሱ። እርሱ ለእናንተ የተሻለ ነው። አላህ የምትሠሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው። መኖሪያ ያልሆኑን ቤቶች ግን በውስጣቸው ለእናንተ ጥቅም ካላችሁ ሳታስፈቅዱ ብትገቡ በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። አላህ የምትገልፁትንም ሆነ የምትደብቁትን ሁሉ ያውቃል።*

* ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አነስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ አሉኝ በማለት፦ «ልጄ ሆይ! ወደ ቤተሰቦችህ ስትገባ ሰላምታ አቅርብ። ላንተም ለቤተሰቦችህም በረከት ይሆንላችኋልና» ብለውኛል ብለዋል።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ፈቃድ መጠየቅ ሶስት ጊዜ ነው። ከተፈቀደልህ ግባ። ካለበለዚያ ግን ተመለስ።»

አቡ ደውድ በዘገቡት ሐዲስ ረቢዕ ኢብኑ ሒራሽ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ አንድ የበኒ ዓሚር ሰው እንደነገረን ነብዩ ከቤታቸው ውስጥ እያሉ እርሱ ሄደና «ልግባ?» ሲል ጠየቀ። እርሳቸውም ለአገልጋያቸው፦ «ውጣና ይህ ሰው እንዴት ፈቃድ መጠየቅ እንዳለበት አስተምረው፦ አስሰላሙ ዐለይኩም ልግባ? እንዲል ንገረው» አሉት። እርሱም ይህን ንግግራቸውን ሰማና፦ «አስሰላሙ ዐለይኩም፤ ልግባ?» አለ። ነብዩ እንዲገባ ፈቀዱለትና ገባ።

አቡዳውድና ቲርሚዚ እንደዘገቡት፦ ኪልደት ኢብኑ ሐንበል እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ «ወደ ነብዩ መጣሁና ሰላምታ ሳላቀርብ እንዲሁ ገባሁባቸው። ነብዩም፦ ተመለስና አሰላሙ ዐለይኩም ልግባ? በል» አሉኝ።

ከብርሃን ምዕራፍ (27-29) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ አንዲት የአንሷር ሴት ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥታ አንዳንድ ጊዜ በቤቴ ውስጥ ማንም አባትም ሆነ ልጅ በማልፈቅድበት ሁኔታ እሆናለሁ። ሆኖም አባቶች በድንገት ይገቡብኛል ምን ይሻለኛል ብላ ስለጠየቀች ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

قُل لِّلْمُؤْمِنِينَ يَغُضُّوا۟ مِنْ أَبْصَٰرِهِمْ وَيَحْفَظُوا۟ فُرُوجَهُمْ ۚ
ذَٰلِكَ أَزْكَىٰ لَهُمْ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرٌۢ بِمَا يَصْنَعُونَ ﴿٣٠﴾

**30.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለምዕመናን ንገራቸው አይኖቻቸውን ከማየት ይከልክሉ። ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ። ይህ ለእነርሱ የተሻለ ነው። አላህ በሚሠሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና።

وَقُل لِّلْمُؤْمِنَٰتِ يَغْضُضْنَ مِنْ أَبْصَٰرِهِنَّ وَيَحْفَظْنَ فُرُوجَهُنَّ وَلَا يُبْدِينَ زِينَتَهُنَّ إِلَّا مَا
ظَهَرَ مِنْهَا ۖ وَلْيَضْرِبْنَ بِخُمُرِهِنَّ عَلَىٰ جُيُوبِهِنَّ ۖ وَلَا يُبْدِينَ زِينَتَهُنَّ إِلَّا لِبُعُولَتِهِنَّ أَوْ ءَابَآئِهِنَّ
أَوْ ءَابَآءِ بُعُولَتِهِنَّ أَوْ أَبْنَآئِهِنَّ أَوْ أَبْنَآءِ بُعُولَتِهِنَّ أَوْ إِخْوَٰنِهِنَّ أَوْ بَنِىٓ إِخْوَٰنِهِنَّ أَوْ بَنِىٓ
أَخَوَٰتِهِنَّ أَوْ نِسَآئِهِنَّ أَوْ مَا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُهُنَّ أَوِ ٱلتَّٰبِعِينَ غَيْرِ أُو۟لِى ٱلْإِرْبَةِ مِنَ ٱلرِّجَالِ أَوِ
ٱلطِّفْلِ ٱلَّذِينَ لَمْ يَظْهَرُوا۟ عَلَىٰ عَوْرَٰتِ ٱلنِّسَآءِ ۖ وَلَا يَضْرِبْنَ بِأَرْجُلِهِنَّ لِيُعْلَمَ مَا يُخْفِينَ مِن
زِينَتِهِنَّ ۚ وَتُوبُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ جَمِيعًا أَيُّهَ ٱلْمُؤْمِنُونَ لَعَلَّكُمْ تُفْلِحُونَ ﴿٣١﴾

**31.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለምእመናትም ንገራቸው አይኖቻቸውን ያልተፈቀደን ከማየት ይከልክሉ። ብልቶቻቸውንም ይጠብቁ። ጌጣቸውንም በእርሷ ግልጽ ከሆነው በስተቀር*1 ሆን ብለው አይግለጡ። ጉፍታዎቻቸውንም በአንገትጌዎቻቸው ያጣፉ። (የውስጥ) ጌጣቸውንም ለባሎቻቸው ወይም ለአባቶቻቸው ወይም ለባሎቻቸው አባቶች ወይም ለወንዶች ልጆቻቸው ወይም ለባሎቻቸው ወንዶች ልጆች ወይም ለወንድሞቻቸው ወይም ለወንድሞቻቸው ወንዶች ልጆች ወይም ለእህቶቻቸው ወንዶች ልጆች ወይም ለሴቶቻቸው*2 (ሙስሊም ሴቶች) ወይም በእጆቻቸው ለያዙት (ባሪያ) ወይም ከወንዶች ለሴት ጉዳይ የሌላቸው ለሆኑ ተከታዮች ወይም ለእነዚያ በሴቶች ሀፍረተ ገላ ላይ ላላወቁ ህጻናት ካልሆነ በስተቀር አይግለፁ። ከጌጣቸውም የሚሸፍኑት ይታወቅ ዘንድ በእግሮቻቸው አይምቱ። ምዕመናኖች ሆይ! ከጀሀነም ቅጣት ትድኑ ዘንድ ሁላችሁም ወደ አላህ ተፀፀቱ።

*1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሶፍያ ቢንት ሸይባ እንዳስተላለፈችው ዓኢሻ፦ «ጉፍታዎቻቸውንም በአንገቶቻቸው ላይ ያጣፉ» (አንኑር፡ 31) የሚለው የቁርአን አንቀፅ ሲወርድ «ሴቶች የነጠላዎቻቸውን ጠርዝ ቀድደው አንገቶቻቸው ላይ አጣፉት» ይሉ ነበር።

*2 ግልፅ የተባለው ነገር ምን እንደ ሆነ ሶስት አይነት ልዩነቶች አሉ።

1. ጌጥ ማለት ከአጊያጩ የተለየ በመሆኑ ልብሶችን ማለት ነው።

2. ከአካሏ ውጭ ያሉ ነገር ግን አይኗ ላይ ኩል፤ ጣቷ ላይ ያለ ቀለበት፤
3. ከአካሏ ውጭ ያሉ ነገሮች ማለት ሲሆን እሱም ፊትና እጅ ማለት ነው ይላሉ።

እዚህ ላይ ሰፊ ጥናት የሚያስፈልገው ቢሆንም በአጭሩ የሚመረጠው ከእሷ ጋር ግንኙነት የሌለው አካልን ነው ማለቱ ነው። ምክንያቱም በቁርኣን አጠቃቀም ስንመለከት ጌጥ ማለት ከውጭ የሚመጣ ነገርን እንጂ ከአካል የተያያዘን አያመለክትም (ምእመናን **31**፤ አል-ከህፍ፡ **7**፤ **46**፤ ጧሃ፡ **87**፤ ቀሶስ፡ **60** እና **79**፤ አስሷፋት፡ **6**) አናቅፅ ብንመለከት ሁሉም ከውጭ የመጣ ነገርን ነው የሚያመለክተው።

وَأَنكِحُواْ ٱلۡأَيَٰمَىٰ مِنكُمۡ وَٱلصَّٰلِحِينَ مِنۡ عِبَادِكُمۡ وَإِمَآئِكُمۡۚ
إِن يَكُونُواْ فُقَرَآءَ يُغۡنِهِمُ ٱللَّهُ مِن فَضۡلِهِۦۗ وَٱللَّهُ وَٰسِعٌ عَلِيمٞ ٣٢

**32.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ከናንተ መካከል ትዳር የሌላቸውን ሰዎች አጋቡ*። ከወንዶች ባሮቻችሁና ከሴቶች ባሮቻችሁም ለጋብቻ ብቁ የሆኑትን ክፍሎች አጋቡ። ድሆች ከሆኑም አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል። አላህ ስጦታው ሰፊና ሁሉን ዐዋቂ ነውና።

* ነብዩ (ﷺ) በሀዲሳቸው እንዲህ ሲሉ ስለ ጋብቻ አስፈላጊነት ይመሰክራሉ፡- «ወጣቶች ሆይ! ማግባት አቅሙ የሆነ ሰው ማግባት አለበት። ዓይናችሁን ከመዋተት የመጠበቂያ ብቸኛ መንገድ ነውና። ከወሲባዊ ፍንገጣም ያድናል። የማግባት አቅም የሌለው መፆም አለበት። ምክንያቱም ፆም ስሜትን ለመቆጣጠር ያስችላል፡» (ቡኻሪ)

ኢስላም ጋብቻን ማበረታታት ብቻ ሳይሆን በጋብቻ ጥላ ስር የሚደረግን የግብረ ስጋ ግንኙነት ምንዳን እንደሚያስገኝ ያስተምራል። ነብዩም እንዲህ ሲሉ ተናረዋል፡- «አንድ ሰው ከባለቤቱ ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ምንዳን ያገኛል። «ስሜቱን ለማርካት በሚያደርገው ምንዳን ያገኛልን?» በማለት ተጠየቁ። ነብዩም (ﷺ) «አንድ ሰው ይህን ድርጊት በሕገ. ወጥ መልኩ (ሀራም) ቢፈፅም ኃጢአት ሰርቷል አትሉምን?» ሲሉ መልሰው ከጠየቁ በኋላ «በተመሳሳይ ሁኔታ በህጋዊ መንገድ (በሀላል ከሚስቱ ጋር) ቢፈፅም ምንዳን ያገኛል።» በማለት መለሱ። ሙስሊም፤

አንዲት ሴት ተገዳ ስትደፈር ውስብስብ ማህበራዊ፤ አካላዊና ስነልቦናዊ ችግሮች ውስጥ ትወድቃለች። ቀሪ ህይወቷ ሊበላሽ ይችላል። እንዲህ ላለው ኢ. ሰብአዊ ድርጊት ኢስላም የማያዳግምና ለሌሎች አስተማሪ የሆነ ቅጣት አስቀምጧል የሞት ቅጣትን። ወኢል ኢብኑ ሐጅር እንዳስተላለፈው፡-

አቡዳውድ በ (**2057**) ኛው ሀዲስ ላይ የዘገቡት «ነብዩ (ﷺ) በሕይወት ሳሉ አንዲት ሴት ለሱብሂ (ንጋት ሶላት) ወደ መስጂድ ስትሄድ አንድ ሰው ይደበድባትና ይደፍራታል። ጩኸቷን ስታሰማ ትቷት ሸሸ። ሰዎች ሲደርሱ የተፈፀመባትን ተናገረች። አሯሩጠው ይዘውት መጡና «ይህ ነውን?» በማለት ሲጠይቋት «አዎን» በማለት አረጋገጠችላቸው። ከዚያም ሰውየውን ወደ አላህ መልዕክተኛ ወሰዱት። ሰውየውም ጥፋቱን አመነ። ነብዩም ሴቲቱን«ሂጂ አንቺ ነፃ ነሽ» በማለት አሰናበቷት። ደፋሪውንም «ወግራችሁ ግደሉ» በማለት አዘዙ።»

ኢስላም እንዲህ ላለው ኢ. ሰብአዊ ድርጊት ያስቀመጠውን ቅጣት ሲሰሙ የሚዘገንናቸው አንዳንዶች አልጠፉም። የሚገርመው እነዚሁ ሰዎች የራሳቸው ሴት ልጆች፤ ሚስታቸው እህታቸው አሊያም እናታቸው ቢደፈሩ የቅጣቶች ሁሉ መጨረሻ እንዲፈፀም መሻታቸው አይቀርም። በተጨማሪም የተደፋሪዋ ቤተሰቦች በሽምግልና ሊታረቁ ቢፈልጉም ኢስላም ይህንን ፊፅሞ አይቀበልም። ምክንያቱም የቅጣት ዋና አላማ ጥፍተኛውን መቅጣት ብቻ ሳይሆን ተመሳሳይ ድርጊቶች እንዳይፈፀሙ መከላከል ነውና። ለዚህ አብነት የሚሆነንን ይህን ሀዲስ እናገኛለን።

ቡኻሪና አቡዳውድ በዘገቡት «በነብዩ (ﷺ) ዘመን አንድ ወጣት ከአሰሪው ሚስት ላይ የግዳጅ ወሲብ ፈፀመ። የወጣቱ አባት ለሴቲቱ ባል አንድ መቶ ፍየልና አገልጋይ በካሳነት ሰጠ። ሰውየውም ካሰውን ተቀበለ። ነብዩ ይህንን ሲሰሙ ካሳው እንዲመለስ በማዘዝ ወጣቱ ላይ የዝሙት ቅጣት አስፈፀመውበታል።

ይህን አባባል ስለ መረጥኩኝ እንጂ ለሁሉም ማለትም ለአስገዳጁም ከቶበተ በሚል ሊሆን ይችላል ያሉም የተፍሲር ምሁራን አሉ።

وَلْيَسْتَعْفِفِ ٱلَّذِينَ لَا يَجِدُونَ نِكَاحًا حَتَّىٰ يُغْنِيَهُمُ ٱللَّهُ مِن فَضْلِهِۦ ۗ وَٱلَّذِينَ يَبْتَغُونَ ٱلْكِتَٰبَ مِمَّا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُكُمْ فَكَاتِبُوهُمْ إِنْ عَلِمْتُمْ فِيهِمْ خَيْرًا ۖ وَءَاتُوهُم مِّن مَّالِ ٱللَّهِ ٱلَّذِىٓ ءَاتَىٰكُمْ ۚ وَلَا تُكْرِهُوا۟ فَتَيَٰتِكُمْ عَلَى ٱلْبِغَآءِ إِنْ أَرَدْنَ تَحَصُّنًا لِّتَبْتَغُوا۟ عَرَضَ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۚ وَمَن يُكْرِههُّنَّ فَإِنَّ ٱللَّهَ مِنۢ بَعْدِ إِكْرَٰهِهِنَّ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٣٣﴾

33. እነዚያም የማግቢያን ጣጣ የማያገኙ ሰዎች አላህ ከችሮታው እስከሚያከብራቸው ድረስ ይጠብቁ እነዚያንም እጆቻችሁ ከጨበጧቸው አገልጋዮች መካከል ገንዘብ ሰጥተው ነጻ ለመውጣት መጻጻፍን የሚፈልጉትን ከነርሱ መልካም ነገርን ብታውቁ (ብታዩ) ተጻጻፏቸው። አላህ ከሰጣችሁ ገንዘብም ስጧቸው። ሴቶች ባሮቻችሁንም መጠበቅን ከፈለጉ የቅርቢቱን ህይወት ጥቅም ለመፈለግ ብላችሁ በዝሙት (ተግባር ላይ) አታስገድዷቸው። የሚያስገድዳቸውም ሰው አላህ ከመገደዳቸው በኋላ ለተገደዱት መሓሪና አዛኝ ነውና።

ከብርሃን ምዕራፍ (33) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሱበይህ የተባለ አንድ ባሪያ አለቃውን ሀለውይጢብ ይባል የነበረ ገንዘብ ከፍሎ ከባርነት ነፃ እንዲያወጣው ጠየቀውና እንቢ አለው። ይህ አንቀፅ በወረደበት ጊዜ መቶ ዲናር ወርቅ እንዲከፈለው ተስማማና ከዚያም ሀያ ዲናር ቀንሶ ሲያቃልልበት ሰማንያውን ከፍሎ ራሱን ነፃ አወጣ።

وَلَقَدْ أَنزَلْنَآ إِلَيْكُمْ ءَايَٰتٍ مُّبَيِّنَٰتٍ وَمَثَلًا مِّنَ ٱلَّذِينَ خَلَوْا۟ مِن قَبْلِكُمْ وَمَوْعِظَةً لِّلْمُتَّقِينَ ﴿٣٤﴾

34. (ሰዎች ሆይ!) ወደ እናንተ አብራሪ የሆኑን አንቀፆች ከእነዚያ ከበፊታችሁ ካለፉትም ምሳሌዎች ዓይነት ምሳሌን ለጥንቁቆች መገሰጫን በእርግጥ አወረድን።

**ከብርሃን ምዕራፍ ከአንቀፅ (27-34) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከግል ቤቱ ውጭ በሆነ ቤት ለመግባት የፈለገ ሁሉ ማስፈቀድ ግዴታው መሆኑን፤
2. መኖሪያ ያልሆኑ ቤቶች ለመግባት የፈለገ ሰው ባያስፈቅድም ችግር አለመኖሩን፤
3. አይን መስበርን ሀፍረተ ገላን መሸፈን ግዴታ ስለመሆኑ፤
4. ሴት ልጅ ጌጦችንና የጌጦቿን ቦታ መሸፈን የማያስቸግራት ካልሆነ በስተቀር መሸፈን ግዴታ ስለመሆኑ፤

5. ሴት ልጅ ያለምንም ጭንቀት ጌጦቿን ልትገልጥላቸው የሚፈቀድላቸው ዘመዶችዋን በግልፅ ማሳወቅ፤
6. ላረጀ ሽማግሌ፤ ለሞኝ ስለ ሀፍረተ ገላ ምንም ላላወቀ ህፃን የጌጥ ቦታዎችን መግለፅ ማሳየቱ ክልክል እንደሌለበት፤
7. ሴት ልጅ በብር አልቦዋ መሬትን እየመታችና እየጮኸች መሄድ ክልክል ስለመሆኑ፤
8. ከየትኛውም ወንጀል አላህን ይቅርታ መጠየቅና ንሰሀ መግባት ግዴታ ስለ መሆኑ፤

۞ ٱللَّهُ نُورُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ مَثَلُ نُورِهِۦ كَمِشْكَوٰةٍ فِيهَا مِصْبَاحٌ ۖ ٱلْمِصْبَاحُ فِى زُجَاجَةٍ ۖ
ٱلزُّجَاجَةُ كَأَنَّهَا كَوْكَبٌ دُرِّىٌّ يُوقَدُ مِن شَجَرَةٍ مُّبَٰرَكَةٍ زَيْتُونَةٍ لَّا شَرْقِيَّةٍ وَلَا غَرْبِيَّةٍ
يَكَادُ زَيْتُهَا يُضِىٓءُ وَلَوْ لَمْ تَمْسَسْهُ نَارٌ ۚ نُّورٌ عَلَىٰ نُورٍ ۚ يَهْدِى ٱللَّهُ لِنُورِهِۦ مَن يَشَآءُ ۚ
وَيَضْرِبُ ٱللَّهُ ٱلْأَمْثَٰلَ لِلنَّاسِ ۗ وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ ﴿٣٥﴾

**35.** አላህ የሰማያትና የምድር (አብሪ) ብርሃን ነው፤ የብርሃኑ ምሳሌ በውስጡ መብራት እንዳለባት ዝግ መስኮት መብራቱ በብርጭቆ ውስጥ የሆነ ብርጭቆው ደግሞ ፍፁም ሉላዊ ኮከብ የምትመስል ምስራቃዊም ምዕራባዊም ካልሆነች፤ ከተባረከች የወይራ ዛፍ ዘይቷ እሳት ባይነካውም እንኳ ሊያበራ የሚቀርብ ከሆነች ዘይት የሚቃጠል እንደሆነ መብራት ነው ይህ በብርሃን ላይ የሆነ ብርሃን ነው። አላህ ወደ ብርሃኑ የሚሻውን ሰው ይመራል፤ አላህም ለሰዎች ምሳሌዎችን ያቀርባል አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ዐዋቂ ነውና።

فِى بُيُوتٍ أَذِنَ ٱللَّهُ أَن تُرْفَعَ وَيُذْكَرَ فِيهَا ٱسْمُهُۥ يُسَبِّحُ لَهُۥ فِيهَا بِٱلْغُدُوِّ وَٱلْـَٔاصَالِ ﴿٣٦﴾
رِجَالٌ لَّا تُلْهِيهِمْ تِجَٰرَةٌ وَلَا بَيْعٌ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ وَإِقَامِ ٱلصَّلَوٰةِ وَإِيتَآءِ ٱلزَّكَوٰةِ ۙ يَخَافُونَ يَوْمًا
تَتَقَلَّبُ فِيهِ ٱلْقُلُوبُ وَٱلْأَبْصَٰرُ ﴿٣٧﴾ لِيَجْزِيَهُمُ ٱللَّهُ أَحْسَنَ مَا عَمِلُوا۟ وَيَزِيدَهُم مِّن فَضْلِهِۦ ۗ
وَٱللَّهُ يَرْزُقُ مَن يَشَآءُ بِغَيْرِ حِسَابٍ ﴿٣٨﴾

**36-38.** አላህ እንዲከበሩና ስሙ በውስጣቸው እንዲወሳ ባዘዘው ቤቶች ውስጥ አወድሱት። በውስጧ በጧትና በማታ ለርሱ ያጠራሉ። አላህን ከማውሳትና ሰላትን ከመስገድ ዘካንም ከመስጠት ንግድም ሽያጭም የማያታልላቸው ልቦችና ዓይኖች በእርሱ የሚገላበጡበትን[*1] ቀን የሚፈሩ የሆኑ ሰዎች ያጠሩታል። አላህ የሰሩትን ስራ መልካሙን ሊመነዳቸው ከችሮታውም ሊጨምርላቸው[*2] ያጠሩታል። አላህ ለሚሻው ሰው ሁሉ ያለ ግምት ይሰጣል።

✴1 መገለባበጥ ማለት በጋፊር ምዕራፍ (18) ኛው አንቀፅ ላይ «ቅርቢቱን የትንሳኤ ቀን ልቦች ጭንቀትን የተሞሉ ሆነው ላንቃዎች ዘንድ የሚደርሱበትን ጊዜ አስጠንቅቃቸው። ለበደለኞች ምንም ወዳጅና ተሰሚ አማላጅ የላቸውም» እንዳለው ሁሉ «በድንጋጤ በምትረበሸበት ማለት ነው» በገሀነም እሳት ስትገላበጥ ማለት ነው ወይም አቋሟን ስትቀየር ማለት ከተጠራጣሪነት ወደ ማረጋገጥ ስትቀየር ማለት ነው» ያሉ አሉ።

✴2 እዚህ ላይ«ሊጨምርላቸው» ያለው ነገር ምን እንደ ሆነ ብዙ ልዩነቶች የተዘገቡ ሲሆን ለኸይር ስራዎች የሚያነባብረው ነገር ሳይሆን ሌላ ነገር እንደሚጨምርላቸው ቃል መግባቱን ያመለክታል የሚለው ነው የሚመረጠው።

وَٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَعۡمَٰلُهُمۡ كَسَرَابِۭ بِقِيعَةٖ يَحۡسَبُهُ ٱلظَّمۡـَٔانُ مَآءً حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَهُۥ لَمۡ يَجِدۡهُ
شَيۡـٔٗا وَوَجَدَ ٱللَّهَ عِندَهُۥ فَوَفَّىٰهُ حِسَابَهُۥۗ وَٱللَّهُ سَرِيعُ ٱلۡحِسَابِ ٣٩

39. እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች መልካም ስራዎቻቸው በበረሃ ሜዳ እንዳለ ሲሪብዱ ነው። ሲሪብዱ ውሃ የጠማው ሰው ውሃ ነው ብሎ እንደሚያስበው በቀረቡት ጊዜ ምንም ነገር ሆኖ እንደማያገኘው ነው፤ (ከሓዲው) አላህን እስራው ዘንድ ያገኘዋል። ምርመራውንም ቅጣቱን ይሞላለታል፤ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው።

أَوۡ كَظُلُمَٰتٖ فِي بَحۡرٖ لُّجِّيّٖ يَغۡشَىٰهُ مَوۡجٞ مِّن فَوۡقِهِۦ مَوۡجٞ مِّن فَوۡقِهِۦ سَحَابٞۚ ظُلُمَٰتُۢ بَعۡضُهَا
فَوۡقَ بَعۡضٍ إِذَآ أَخۡرَجَ يَدَهُۥ لَمۡ يَكَدۡ يَرَىٰهَاۗ وَمَن لَّمۡ يَجۡعَلِ ٱللَّهُ لَهُۥ نُورٗا فَمَا لَهُۥ مِن نُّورٍ ٤٠

40. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወይም መጥፎ ስራዎቻቸው ከበላዩ ማዕበል ከበላዩ ደመና ያለበት ማዕበል በሚሸፍነው ጥልቅ ባህር ውስጥ እንዳሉ ጨለማዎች ነው። እነዚያ ከፊላቸው ከከፊሉ በላይ ድርብርብ የሆኑ ጨለማዎች ናቸው። በዚህች የተሞከረ ሰው እጁን ባወጣ ጊዜ ሊያያት አይደርስም።✴ አላህ ብርሃንን ያላደረገለት ሰው ሁሉ ለእርሱ ምንጊዜም ምንም ብርሃን የለውም።

✴ በቁርአን ውስጥ ካሉ ሳይንሳዊ ተዓምራት መካከል በዚህ አንቀፅ የተጠቀሰው እውነታ መሆኑን፤ የባህር ጥልቀቱ ሲጨምር እየጠፋ እንደሚሄድ፡- ከ 1000 ሜትር ጥልቀት ወደ ታች በምንም አይነት ብርሀን እንደሌለ ተደራራቢ የጨለማ ሽፋኖችን የሚፈጥሩ የውስጥ ሀይለኛ ሞገዶች መኖራቸውን ሳይንስ የተራቀቁ መሳሪያዎቹን ተጠቅሞ የደረሰበትን ግኝት ክፍለ ዘመናትን ያስቀጠረው ቁርአን በሱረቱ አንኑር፡ (40) አስነብቧል። ይህን ሀቅ በገፅ (204) በዝርዝር አስፍሮት ይገኛል።

أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يُسَبِّحُ لَهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱلطَّيۡرُ صَٰٓفَّٰتٖۖ كُلّٞ قَدۡ عَلِمَ صَلَاتَهُۥ
وَتَسۡبِيحَهُۥۗ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِمَا يَفۡعَلُونَ ٤١

**41.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማያትና በምድር ያለ ሁሉ በራሪዎችም ክንፎቻቸውን በአየር ላይ ያንሳፈፉ ሆነው ለእርሱ የሚያጠሩ የሚያወድሱ መሆናቸውን አላወቅህምን? ሁሉም ስግደቱንና* ማጥራቱን በእርግጥ ዐወቀ። አላህ የሚሰሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነውና።

* እያንዳንዱ ሰጋጅ የራሱን ሶላት ያውቃል ማለት ነው የሚለው ተፍሲር አላህ የእያንዳዱን ሶላት ያውቃል ከማለት የተመረጠ ነው።

وَلِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ وَإِلَى ٱللَّهِ ٱلۡمَصِيرُ ﴿٤٢﴾

**42.** የሰማያትም ሆነ የምድር ግዛት የአላህ ነው። መመለሻም ወደ አላህ ነው።

أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يُزۡجِي سَحَابٗا ثُمَّ يُؤَلِّفُ بَيۡنَهُۥ ثُمَّ يَجۡعَلُهُۥ رُكَامٗا فَتَرَى ٱلۡوَدۡقَ يَخۡرُجُ مِنۡ
خِلَٰلِهِۦ وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن جِبَالٖ فِيهَا مِنۢ بَرَدٖ فَيُصِيبُ بِهِۦ مَن يَشَآءُ وَيَصۡرِفُهُۥ عَن
مَّن يَشَآءُۖ يَكَادُ سَنَا بَرۡقِهِۦ يَذۡهَبُ بِٱلۡأَبۡصَٰرِ ﴿٤٣﴾ يُقَلِّبُ ٱللَّهُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ
لَعِبۡرَةٗ لِّأُوْلِي ٱلۡأَبۡصَٰرِ ﴿٤٤﴾

**43-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ደመናን የሚነዳ መሆኑን አላየህምን? ከዚያ ከፊሉን ከከፊሉ ያገናኛል ከዚያ የተደራረበ ያደርገዋል፤ ዝናቡንም ከመካከሉ የሚወጣ ሆኖ ታየዋለህ፤ ከሰማይም ከደመና በውስጡ ካሉት ጋራዎች በረዶን ያወርዳል በርሱም የሚሻውን ሰው በጉዳት ይነካል። ከሻውም ሰው ላይ ይመልሰዋል። የብልጭታው ብርሃን ዓይኖችን ሊወስድ ይቀርባል። አላህ ሌሊትንና ቀንን ያገላብጣል፤ በዚህም ለባለ ውስጥ ዓይኖች በእርግጥ ማስረጃ አለበት።

وَٱللَّهُ خَلَقَ كُلَّ دَآبَّةٖ مِّن مَّآءٖۖ فَمِنۡهُم مَّن يَمۡشِي عَلَىٰ بَطۡنِهِۦ وَمِنۡهُم مَّن يَمۡشِي عَلَىٰ رِجۡلَيۡنِ
وَمِنۡهُم مَّن يَمۡشِي عَلَىٰٓ أَرۡبَعٖۚ يَخۡلُقُ ٱللَّهُ مَا يَشَآءُۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ﴿٤٥﴾

**45.** አላህም ተንቀሳቃሽን ሁሉ ከውሃ ፈጠረ። ከእነርሱም መካከል በሆዱ ላይ የሚሄድ አለ፤ ከእነርሱም መካከል በሁለት እግሮቹ ላይ የሚሄድ አለ፤ ከእነርሱም መካከል በአራት እግሩ የሚሄድ አለ። አላህ የሚሻውን ሁሉ ይፈጥራል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

**ከብርሃን ምዕራፍ ከአንቀፅ (35-45) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኸይር የተባለ ሁሉ ከአላህ ብቻ እንደሚገኝ፤
2. መልዕክቶችን ለማስረዳት ምሳሌዎችን ማምጣት ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. የኢስላም ሃይማኖት አይሁድም ሆኑ ነሷራ ካፒታሊስትም ሆነ ኮሚኒስት እንዳልሆነ ማመልከት፤
4. የአላህን መስጂዶች ማክበርና መንከባከብ ግዴታ ስለመሆኑ፤
5. ንግድና ገበያ ያላታለላቸውን ሰዎች ማሞገስ፤
6. ነገሮችን በምሳሌ ማስረዳት ተገቢ ስለመሆኑ፤
7. ከሓዲያን በሁሉ ነገር ከሳሪ መሆናቸውን፤
8. ካፊሮች በድንቁርናና በክህደት በግፍ ጨለማዎች ውስጥ እንደሚኖሩ፤
9. አላህ ብርሃኑን ያልሰጣቸው ሰዎች ምንም አይነት ብርሃን እንደሌላቸው እንማራለን።

لَّقَدْ أَنزَلْنَآ ءَايَٰتٍ مُّبَيِّنَٰتٍۚ وَٱللَّهُ يَهْدِى مَن يَشَآءُ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٤٦﴾

**46.** አብራሪን አንቀፆች በእርግጥ አወረድን አላህ የሚሻውን ሰው ወደ ቀጥተኛ መንገድ ይመራዋል።

وَيَقُولُونَ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَبِٱلرَّسُولِ وَأَطَعْنَا ثُمَّ يَتَوَلَّىٰ فَرِيقٌ مِّنْهُم مِّنۢ بَعْدِ ذَٰلِكَۚ وَمَآ أُوْلَٰٓئِكَ بِٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٤٧﴾ وَإِذَا دُعُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ لِيَحْكُمَ بَيْنَهُمْ إِذَا فَرِيقٌ مِّنْهُم مُّعْرِضُونَ ﴿٤٨﴾ وَإِن يَكُن لَّهُمُ ٱلْحَقُّ يَأْتُوٓاْ إِلَيْهِ مُذْعِنِينَ ﴿٤٩﴾ أَفِى قُلُوبِهِم مَّرَضٌ أَمِ ٱرْتَابُوٓاْ أَمْ يَخَافُونَ أَن يَحِيفَ ٱللَّهُ عَلَيْهِمْ وَرَسُولُهُۥۚ بَلْ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٥٠﴾

**47-50.** በአላህና በመልዕክተኛው አምነናል ታዘናልም ይላሉ። ከዚያ ከዚህ በኋላ ከእነርሱ ከፊሉ ይሸሻል። እነዚያም አማኞች አይደሉም። ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛውም በመካከላቸው ለሚከሰቱ ጉዳዮች ሊፈርድ በተጠሩ ጊዜ ከእነርሱ መካከል ከፊሉ ወዲያውኑ ይሸሻሉ። እውነትም ሐቁ ለእነርሱ ቢሆን ወደ እርሱ ታዛዦች ሆነው ይመጣሉ። በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ አለን? ወይስ በነብይነት ተጠራጠሩን? ወይስ አላህና መልዕክተኛው በእነርሱ ላይ የሚበድሉ መሆንን ይፈራሉን? ይልቁንም እነዚያ እነርሱ በዳዮች ናቸው።

ከብርሃን ምዕራፍ (47) ኛው አንቀፅ ወረደበት ምክንያት፡- በአስመሳዮች ምክንያት መውረዱን ቀታዳ የተባሉ ዓሊም ሲናገሩ በተለይም ግሽን የተባለ አስመሳዮች ከአንድ አይሁድ ጋር ተጣልቶ በመሀከላቸው ለተፈጠረው ችግር ነብዩ እንዲዳኟቸው አይሁዱ ሲጠይቀው ሙናፊቁ ግን ሀሰት እንደያዘ ስለሚያውቅና ነብዩ በትክክል የሚፈርዱ በመሆናቸው እና በሱ ላይ እንደሚፈርዱበት አውቆ የአይሁዶች አለቃ ወደ ነበረው ካዕብ ኢብኑ አሽረፍ ወደ ተባለ ዩሁዳዊ ጉዳዩን እንዲወስዱ አግባባው። እንቢ ብሎ ጉዳዩን ወደ ነብዩ ወስዶ ነብዩ ሲፈርዱበት ሙናፊቁ በነብዩ ውሳኔ ሳይረካ ፈርዱን በመቃወም ወደ ዑመር እንሂድ አለው። አይሁዱም ለዑመር «ነብዩ ለእኔ ፈረዱልኝ እሱ ግን አልተቀበለምና ወደ አንተ መጣን» አላቸው። ዑመርም ለሙናፊቁ «ጠብቀኝ» አሉትና ወደቤታቸው

በመግባት ሰይፋቸውን ይዘው የሙናፊቁን አንገት ቆርጠው ገደሉት። «የአላህንና የመልዕክተኛውን ፍርድ ላልተቀበለ ሰው ሁሉ እንዲህ ነው የምፈርደው» አሉ። በዚህ ጊዜ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። መልዐኩ ጅብሪል «ዑመር እውነትን ከውሸት የለየነው» በማለቱ ነው ፋሩቅ የሚለውን ስያሜ ያገኙት። በሙጊራት ቢን ዋኢልና ቢን አቡጧሊብ መካከል በመሬት የተነሳ ከፍተኛ ክርክር ነበር። ሲከፋፈሉ ለዓሊይ ውሃ እንደልቡ የማይደርሰው ክፍል ደርሳቸው። በዚህ ጊዜ ሙጊራህ መሬትን ቢሸጥልኝ አላቸውና ሸጡለት። ሰዎች መጥተው ውሃ እንደልቡ የማይደርሰውን መሬት ነው የገዛው ሲሉት «እንደገና መልስልኝ እኔ ስለ ወደድኩት ነበር የገዛሁት አሁን ደስ ስላለኝ መልስልኝ» አላቸው። ዓሊይም «ወደህ አውቀህና አምነህበት ነው የገዛኸው። አሉ። «እሺ ለዚህ ጉዳይ ነብዩ ይዳኙኝ» ሲሉት ሰውየውም «ሙሐመድ ስለሚጠላኝ ያዳላብኛል» ብሎ ስለጠረጠራቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

إِنَّمَا كَانَ قَوْلَ ٱلْمُؤْمِنِينَ إِذَا دُعُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ لِيَحْكُمَ بَيْنَهُمْ أَن يَقُولُواْ سَمِعْنَا وَأَطَعْنَاۚ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٥١﴾

51. የምዕምናን ቃል ግን የነበረው ወደ አላህና ወደ መልዕክተኛው በመካከላቸው ሊፈርድ በተጠሩ ጊዜ ሰማን ታዘዝንም ማለት ብቻ ነው። እንዚህ ማለት እነርሱ የፈለጉትን የሚያገኙ ናቸው።

وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَيَخْشَ ٱللَّهَ وَيَتَّقْهِ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْفَآئِزُونَ ﴿٥٢﴾

52. አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው አላህንም የሚፈራና ቁጣውን የሚጠነቀቀው ሰው፤ ፍላጎታቸውን የሚያገኙ እነዚያ እነርሱ ናቸው።

۞ وَأَقْسَمُواْ بِٱللَّهِ جَهْدَ أَيْمَٰنِهِمْ لَئِنْ أَمَرْتَهُمْ لَيَخْرُجُنَّۖ قُل لَّا تُقْسِمُواْۖ طَاعَةٌ مَّعْرُوفَةٌۚ إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿٥٣﴾

53. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለዘመቻ ብታዛቸው በእርግጥ እንደሚወጡ የጠነከሩ መሓላዎቻቸውን በአላህ ስም ይምላሉ፤ አትማሉ። የታወቀ የንፍቅና መታዘዝ ነው። አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ ዐዋቂ ነው በላቸው።

قُلْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَۖ فَإِن تَوَلَّوْاْ فَإِنَّمَا عَلَيْهِ مَا حُمِّلَ وَعَلَيْكُم مَّا حُمِّلْتُمْۖ وَإِن تُطِيعُوهُ تَهْتَدُواْۚ وَمَا عَلَى ٱلرَّسُولِ إِلَّا ٱلْبَلَٰغُ ٱلْمُبِينُ ﴿٥٤﴾

54. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህንና መልዕክተኛውንም ታዘዙ። ብትሸሹም አትጎዱትም። በእርሱ ላይ ያለበት የተገደደውን ማድረስ ብቻ ነው። በእናንተም ላይ ያለባችሁ የተገደዳችሁትን መታዘዝ ብቻ ነው። ብትታዘዙት ወደ ቀናው መንገድ ትመራላችሁ በመልዕክተኛው ላይ ግልጽ ማድረስ እንጂ ሌላ የለበትምና በላቸው።

وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنكُمۡ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَيَسۡتَخۡلِفَنَّهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ كَمَا ٱسۡتَخۡلَفَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ وَلَيُمَكِّنَنَّ لَهُمۡ دِينَهُمُ ٱلَّذِي ٱرۡتَضَىٰ لَهُمۡ وَلَيُبَدِّلَنَّهُم مِّنۢ بَعۡدِ خَوۡفِهِمۡ أَمۡنٗاۚ يَعۡبُدُونَنِي لَا يُشۡرِكُونَ بِي شَيۡـٔٗاۚ وَمَن كَفَرَ بَعۡدَ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡفَٰسِقُونَ ﴿٥٥﴾

**55.** አላህ እነዚያን ከናንተ መካከል በትክክል ያመኑትንና መልካም ስራዎችን የሰሩትን እነዚያን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን እንደተካቸው ሁሉ በምድር ላይ በእርግጥ ሊተካቸው፤ ለእነርሱም ያን የወደደላቸውን ሃይማኖታቸውን ሊያደላድልላቸው፤ ከፍርሃታቸውም በኋላ ፀጥታን ሊለውጥላቸው የተስፋን ቃል ሰጥቷቸዋል። በእኔ ምንንም የማያጋሩ ሆነው ይገዙኛል፤ ከዚያ በኋላ በሱ የካዱ ሰዎች እነዚያ አመፀኞች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው።

ከብርሃን ምዕራፍ (55) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በመካ በፍርሃት ሲጨነቁ በነበሩትና ከዚያም ይህ ቀን አልፎ ሰላም የምናገኝበት ጊዜ ይመጣ ይሆን እያሉ ሲጠይቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

وَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ﴿٥٦﴾

**56.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ይታዘንላችሁ ዘንድ ሶላትን አስተካክላችሁ ስገዱ። ምጽዋትንም ስጡ፤ መልዕክተኛውንም ታዘዙ፤

لَا تَحۡسَبَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مُعۡجِزِينَ فِي ٱلۡأَرۡضِۚ وَمَأۡوَىٰهُمُ ٱلنَّارُۖ وَلَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ﴿٥٧﴾

**57.** እነዚያ በአላህ የካዱትን በምድር ውስጥ የሚያቅቱ አድርገህ አታስብ መኖሪያቸው እሳት ናት። ገሀነም በእርግጥም ምን ትከፋ።

**ከብርሃን ምዕራፍ ምዕራፉ ከአንቀፅ (46-57) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ችሎታውና እውቀቱ እንዲሁም ጥበቡ የሚታይባቸው ክንውኖች፤
2. የዝናብና የበረዶ አመጣጥ ሁኔታን መግለፅ፤
3. አላህ ለባሮቹ ያለውን እዝነት የሚያሳዩ ሁኔታዎች፤
4. ሌሊትንና ቀንን በማቀያየር አላህ ያለውን ችሎታና እውቀት በግልፅ ማሳየት፤
5. ፍጡራን ከውሃ ተፈጥረው በአንድ ደረጃ የተለያዩ እንደሆኑ፤
6. አላህ የተለያዩ አናቅፅን በማውረድ መመፃደቁ፤
7. የቁርአንና የሀዲስን ዳኝነት መቀበል ግዴታ ስለመሆኑ፤
8. ወደ ቁርአንና ሀዲስ ዳኝነት ተጠርቶ እምቢ ያለ በግልፅ አስመሳዮች ስለመሆኑ፤
9. ቁርአንና ሀዲስን ትቶ በምድራዊ ህጎች መዳኘት የክህደትና የንፍቅና ምልክት መሆኑን
10. በአላህ መማል ተገቢ መሆኑን በሌላ ግን መማል እንደሚከለከል፤
11. ለአስመሳዮች ምንንም ደግ ማድረግ እንደማይቻል፤
12. የአላህን መልዕክተኛ (ﷺ) መታዘዝ ለሁለት አለም ምቾት ሲያበቃ አለመታዘዝ ደግሞ ለሁለት አለም ኪሳራ እንደሚያደርግ፤

13. ትክክለኛ እምነት ይዘው መልካም ስራ ለሰሩ የነብዩ (ﷺ) ሶሃባዎች (ባልደረቦቻቸው) የገባላቸውን ቃል መፈፀሙ፤
14. አላህ ለሚውላቸው ፀጋዎች ማመስገን ግዴታ ስለመሆኑ፤
15. (የአላህን) ውለታዎች የካደና ያስተባበለ የሚጠብቀው ከፍተኛ ቅጣት፤
16. ሶላት መስገድ፤ ዘካ መስጠትና ነቢዩ ሙሐመድን (ﷺ) መታዘዝ ግዴታ ስለመሆኑ፤
17. ካፊሮች የቱንም ያህል ኃይል ቢኖራቸው አላህን እንደማያሸንፉ እንማራለን።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لِيَسۡتَـٔۡذِنكُمُ ٱلَّذِينَ مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُكُمۡ وَٱلَّذِينَ لَمۡ يَبۡلُغُواْ ٱلۡحُلُمَ مِنكُمۡ ثَلَٰثَ مَرَّٰتٖۚ مِّن قَبۡلِ صَلَوٰةِ ٱلۡفَجۡرِ وَحِينَ تَضَعُونَ ثِيَابَكُم مِّنَ ٱلظَّهِيرَةِ وَمِنۢ بَعۡدِ صَلَوٰةِ ٱلۡعِشَآءِۚ ثَلَٰثُ عَوۡرَٰتٖ لَّكُمۡۚ لَيۡسَ عَلَيۡكُمۡ وَلَا عَلَيۡهِمۡ جُنَاحُۢ بَعۡدَهُنَّۚ طَوَّٰفُونَ عَلَيۡكُم بَعۡضُكُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖۚ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمُ ٱلۡأٓيَٰتِۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ﴿٥٨﴾ وَإِذَا بَلَغَ ٱلۡأَطۡفَٰلُ مِنكُمُ ٱلۡحُلُمَ فَلۡيَسۡتَـٔۡذِنُواْ كَمَا ٱسۡتَـٔۡذَنَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ لَكُمۡ ءَايَٰتِهِۦۗ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ﴿٥٩﴾

**58-59.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! እነዚያ እጆቻችሁ የጨበጧቸው ባሮች እነዚያም ከናንተ መካከል ለአካለ መጠን ያልደረሱት ህፃናት ከጎህ ስግደት በፊት፤ በቀትር ልብሶቻችሁን በምታወልቁበት ጊዜና ከምሽት ስግደትም በኋላ በሶስት ጊዜያት ወደ እናንተ ለመግባት ሲፈልጉ ያስፈቅዷችሁ። እነዚህ የእናንተ ሶስት የሐፍረተ ገላ መገለጫ ጊዜያቶች ናቸውና። ከእነዚህ ግን በእናንተም ሆነ በነሱ ላይ (ያለፈቃድ በመግባት) ኃጢአት የለም። እናንተን ለማገልገል በዙሪያችሁ ዟሪዎች ናቸውና። ከፊላችሁ በከፊሉ ላይ ዟሪ ነውና፤ ልክ እንደዚሁ አላህ ለእናንተ ህግጋትን ይገልጽላችኋል። አላህ ሁሉን ዐዋቂና ጥበበኛ ነውና። ከናንተም ህጻናቶቹ መካከል ለአቅመ አዳም በደረሱ ጊዜ እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ታላላቆች እንዳስፈቀዷችሁ ያስፈቅዱ። ልክ እንደዚሁ አላህ ለእናንተ አንቀፆችን ያብራራል። አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነው።

وَٱلۡقَوَٰعِدُ مِنَ ٱلنِّسَآءِ ٱلَّٰتِي لَا يَرۡجُونَ نِكَاحٗا فَلَيۡسَ عَلَيۡهِنَّ جُنَاحٌ أَن يَضَعۡنَ ثِيَابَهُنَّ غَيۡرَ مُتَبَرِّجَٰتِۭ بِزِينَةٖۖ وَأَن يَسۡتَعۡفِفۡنَ خَيۡرٞ لَّهُنَّۗ وَٱللَّهُ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ﴿٦٠﴾

**60.** (ሙስሊሞች ሆይ!) ከሴቶችም እነዚያ ጋብቻን የማይፈልጉት ባልቴቶች በጌጥ የተገለፁ ሳይሆኑ የላይ ልብሶቻቸውን ቢጥሉ በእርሱ ላይ ኃጢአት የለባቸውም። ግን መጠበቃቸው ለእነርሱ የተሻለ ነው።

ከብርሃን ምዕራፍ ከ (58-60) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረደቡት ምክንያት በተመለከተ የተለያዩ ዘገባዎች አሉ። እነሱም፡- (ሀ) አስማእ ቢንት አቡመስር በተባለች ሴትዮ ምክንያት እና፤ (ለ) በኡመር ኢብኑል ኸጣብ ምክንያት የሚሉት ናቸው።

لَّيۡسَ عَلَى ٱلۡأَعۡمَىٰ حَرَجٞ وَلَا عَلَى ٱلۡأَعۡرَجِ حَرَجٞ وَلَا عَلَى ٱلۡمَرِيضِ حَرَجٞ
وَلَا عَلَىٰٓ أَنفُسِكُمۡ أَن تَأۡكُلُواْ مِنۢ بُيُوتِكُمۡ أَوۡ بُيُوتِ ءَابَآئِكُمۡ أَوۡ بُيُوتِ أُمَّهَٰتِكُمۡ
أَوۡ بُيُوتِ إِخۡوَٰنِكُمۡ أَوۡ بُيُوتِ أَخَوَٰتِكُمۡ أَوۡ بُيُوتِ أَعۡمَٰمِكُمۡ أَوۡ بُيُوتِ عَمَّٰتِكُمۡ
أَوۡ بُيُوتِ أَخۡوَٰلِكُمۡ أَوۡ بُيُوتِ خَٰلَٰتِكُمۡ أَوۡ مَا مَلَكۡتُم مَّفَاتِحَهُۥٓ أَوۡ صَدِيقِكُمۡۚ
لَيۡسَ عَلَيۡكُمۡ جُنَاحٌ أَن تَأۡكُلُواْ جَمِيعًا أَوۡ أَشۡتَاتٗاۚ فَإِذَا دَخَلۡتُم بُيُوتٗا
فَسَلِّمُواْ عَلَىٰٓ أَنفُسِكُمۡ تَحِيَّةٗ مِّنۡ عِندِ ٱللَّهِ مُبَٰرَكَةٗ طَيِّبَةٗۚ كَذَٰلِكَ يُبَيِّنُ ٱللَّهُ
لَكُمُ ٱلۡأٓيَٰتِ لَعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ٦١

**61.** (ከሰዎች ጋር በመብላት) በዕውር (አይነስውር) ላይ ኃጢአት የለበትም፤ በአንካሳም ላይ ኃጢአት የለበትም። በበሽተኛም ላይ ኃጢአት የለበትም። በነፍሶቻችሁም ላይ ከቤቶቻችሁ ወይም ከአባቶቻችሁ ቤቶች ወይም ከእናቶቻችሁ ቤቶች ወይም ከውድሞቻችሁ ቤቶች ወይም ከእህቶቻችሁ ቤቶች፤ ወይም ከአባት ወንድሞች አጎቶቻችሁ ቤቶች፤ ወይም ከአባት እህቶች አክስቶቻችሁ ቤቶች ወይም ከእናት ወንድሞች የሹሞቻችሁ ቤቶች፤ ወይም ከእናት እህቶች ከየሹሜዎቻችሁ ቤቶች ወይም መክፈቻዎችን ከያዛችሁት ቤት ወይም ከወዳጃችሁ ቤት ብትበሉ ኃጢአት የለባችሁም። ተሰብስባችሁ ወይም ተለያይታችሁ ብትበሉ በእናንተ ላይ ምንም ኃጢአት የለባችሁም። ቤቶችንም በገባችሁ ጊዜ ከአላህ ዘንድ የሆነችን የተባረከች መልካም ሰላምታ በነፍሶቻችሁ ላይ ሰላም በሉ። ልክ እንደዚህ አላህ አንቀፆችን ለእናንተ ያብራራል፤ ልታውቁ ይከጀላልና።

ከብርሃን ምዕራፍ (61) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በአል በቀራህ (188) ኛው አንቀፅ ሲወርድ ሙስሊሞች ከደካሞች ጋር መመገብን ጠሉ እና መልካሙን ምግብ መርጠን ስንበላ አይነስውሩ ደግሞ ይህን ሊያደርግ አይችልም ሌሎችም በሽተኞች ከእኛ ጋር ተጋፍተው መብላት አይችሉም ስለዚህ ከእነሱ ጋር መመገብ የለብንም ስላሉ ነው። በእነዚህ በተጠቀሱት ክፍሎች ቤት ሄዳችሁ መመገብ ትችላላችሁ ለማለት ነው። እነዚህ የተጠቀሱት ችግረኞች ጂሃድ ባይሄዱ ምንም ወቀሳ እንደሌለባቸው ለማስታወስ ነው ተብሏል።

إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَإِذَا كَانُواْ مَعَهُۥ عَلَىٰٓ أَمْرٍ جَامِعٍ لَّمْ يَذْهَبُواْ حَتَّىٰ
يَسْتَـْٔذِنُوهُ ۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَسْتَـْٔذِنُونَكَ أُوْلَـٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ ۚ فَإِذَا ٱسْتَـْٔذَنُوكَ
لِبَعْضِ شَأْنِهِمْ فَأْذَن لِّمَن شِئْتَ مِنْهُمْ وَٱسْتَغْفِرْ لَهُمُ ٱللَّهَ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٦٢﴾

62. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ትክክለኛ ምዕመናን ማለት እነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው ያመኑት። ከመልዕክተኛው ጋር በሚሰበሰብ ጉዳይ ላይ በሆኑ ጊዜ እስከሚያስፈቅዱት ድረስ የማይሄዱት ብቻ ናቸው፤ እነዚያ የሚያስፈቅዱህ እርሱ እነዚያ በትክክል በአላህና በመልዕክተኛው የሚያምኑት ናቸው። ለግል ጉዳያቸውም ፈቃድ በጠየቁህ ጊዜ ከእነርሱ ላሻኸው ሰው ፍቀድለት። ለእነርሱም ከአላህ ምህረትን ለምንላቸው። አላህ መሓሪና አዛኝ ነውና።

لَّا تَجْعَلُواْ دُعَآءَ ٱلرَّسُولِ بَيْنَكُمْ كَدُعَآءِ بَعْضِكُم بَعْضًا ۚ قَدْ يَعْلَمُ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ يَتَسَلَّلُونَ
مِنكُمْ لِوَاذًا ۚ فَلْيَحْذَرِ ٱلَّذِينَ يُخَالِفُونَ عَنْ أَمْرِهِۦٓ أَن تُصِيبَهُمْ فِتْنَةٌ أَوْ يُصِيبَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٦٣﴾

63. (አማኞች ሆይ) በመካከላችሁ የመልዕክተኛውን ጥሪ ከፊላችሁ ከፊሉን እንደመጥራት አታድርጉት። ከናንተ ውስጥ እነዚያን እየተከለሉ በመሹሎክሎክ የሚወጡትን አላህ በእርግጥ ያውቃቸዋል። እነዚያም ትእዛዙን የሚጥሱ ሁሉ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ።

أَلَآ إِنَّ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ قَدْ يَعْلَمُ مَآ أَنتُمْ عَلَيْهِ وَيَوْمَ يُرْجَعُونَ إِلَيْهِ
فَيُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُواْ ۗ وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌۢ ﴿٦٤﴾

64. (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተንትኑ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ብቻ ነው። እናንተ በእርሱ ላይ ያላችሁበትን ሁኔታ በእርግጥ ያውቃል። ወደ እርሱ የሚመለሱበትን ቀንም ያውቃል። ከዚያ የሰሩትንም ሁሉ ይነግራቸዋል። አላህ ነገሩን ሁሉ ዐዋቂ ነውና።

**ከብርሃን ምዕራፍ ከአንቀፅ (58-64) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አባቶቻችንና አስተዳዳሪዎቻችን እንዲሁም ህፃናትና ሰራተኞችን በሶላት ሰዓት ማስፈቀድ ግዴታ እንዳለባቸው ማስተማር፤
2. ልጆች በህልማቸው የዘር ፈሳሽ ካዩ ወደ ቤታቸው የሚመጡ ሰዎች ሁሉ አስፈቅደው መግባት እንዳለባቸው፤

3. ለወር አበባና ለመውለድ ያልደረሰች ሴት ለባዕድ ወንዶች ፊቷን መግለፅ እንደሚፈቀድላት
4. ከአካል ጉዳተኞች ጋር መመገብ ችግር እንደሌለውና ሙሉ ፈቃድ እንደተሰጠ፤
5. በአካል ጉዳተኞች ቤት መመገብ ችግር የሌለበት መሆኑን፤
6. በተናጠልም ሆነ በህብረት መመገብ እንደሚቻል፤
7. ወደ ቤት ሲገቡ ሰላምታ መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ፤
8. ሁሉን በሚመለከት ጉዳይ መፍቀድ ያለበት ኢማሙ መሆኑን፤
9. ነብዩን (ﷺ) ማክበር ግዴታ ስለ መሆኑ፤
10. የነብዩን (ﷺ) ሱና የሚያደፋፍንና የሚንቅ መጥፎ አሟሟት እንደሚያሰጋው እንማራለን።

በአላህ (عَزَّوَجَلَّ) ፈቃድ የብርሃን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (25)
# እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ
# (ሱረቱ አል-ፉርቃን)

سُورَةُ الفُرۡقَانِ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (77) ናቸው።
### የሱረቱ አል ፉርቃን መግቢያ

የቁርኣንን ትልቅነትና እሱን ያወረደውን ጌታ የአላህን ትልቅነት የሚያሳዩ ነገሮችን ካወሳ በኋላ አጋሪዎች ከአላህ ጋር ጣኦታትን የሚያመልኩና በቁርኣን የሚያስተባብሉ፤ የነብዩን ነብይነት ሰው መሆናቸውን ምክንያት አድርገው የሚያስተባብሉ፤ መላኢኮች መጥተው መልዕክት እንዲያደርሱላቸውም እንደጠየቁና ቁርኣን ተስፋፍቶ መውረዱንም እንደተቃወሙ ምክንያቱን ጭምር በግልፅ ያስቀምጣል። ነብያትና የተላኩላቸው ሰዎች መካከል ያለፉ ታሪኮችን በመግለፅ ሰዎች ስሜታቸውን ሲከተሉ ከእንስሳ በታች እንደሚሆኑ ያስረዳል። በስተመጨረሻም የጀነት ወራሾች ሙዕሚኖች እንደሆኑ በመግለፅ ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

تَبَارَكَ ٱلَّذِي نَزَّلَ ٱلۡفُرۡقَانَ عَلَىٰ عَبۡدِهِۦ لِيَكُونَ لِلۡعَٰلَمِينَ نَذِيرًا ١

**1. ያ፣ ፉርቃንን* (እውነትን ከውሸት የሚለየውን) ቁርአን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይሆን ዘንድ ያወረደው (አምላክ) ክብሩ ይስፋ ጥራት ይገባው።**

* ይህ ስም ከቁርአን ስሞች አንዱ ነው። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ነገር ቢኖር ማንኛውም ነገር የራሱ የሆነ መጠሪያ ስም አለው። በተለይ ደግሞ ለአንድ ነገር የሚሰጠው ስያሜና ባህሪው በተለያየ መልኩ ተደጋግሞ መገለፁ የነገሩን ታላቅነት ያሳየናል። ለምሳሌ፡- የትንሳኤ ቀን በተለያዩ ስሞች መገለፁ የቀኑን ክብደት አግዝፎ ያሳያል።

እንደዚሁም የነብያችን (ﷺ) ስሞችም ብዙ መሆናቸው በአላህ ዘንድ ያላቸውን ወደር የለሽ ክብርና ታላቅነት ያሳየናል።

የአላህ ስሞች በቁርአን ውስጥ በተለያየ ሁኔታ መገለፃቸው የእርሱን ምሉዕነትና ሀያልነት ያሳያሉ። እናም የቁርአን ስሞችና ባህሪያት ብዙ መሆናቸው የቁርአንን ታላቅነት አጉልቶ ያሳያል። የቁርአን ስሞችና ባህሪያት በራሱ በቁርአን የተዘረዘረ ከመሆኑም በላይ ባህሪያቱ ከተልዕኮው ጋር የተዛመዱና የተጣጣሙ ናቸው። ከብዙ ስሞቹና ባህሪያቱ መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል።

1. ቁርአን «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ሰዎችና ጋኔኖች የዚህን ቁርአን ቢጤ በማምጣት ላይ ቢሰበሰቡ ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳት ቢሆኑም እንኳ ብጤውን አያመጡም በላቸው።» (አል. ኢስራእ፡ 88)
2. ፉርቃን እውነትን ከውሸት የሚለየውን «ቁርአን በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይሆን ዘንድ ያወረደው አምላክ ክብሩ ይስፋ ጥራት ይገባው።» (አል. ፉርቃን፡ 1)
3. መገሰጫ «እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ዘንድ ግሳጼ በደረቶች ውስጥም ላለው የመጠራጠር በሽታ ፍቱን መድህኒት፤ ለምዕምናንም ብርሃንና እዝነት የሆነ መልዕክት በእርግጥ መጣላችሁ።» (ዩኑስ፡ 57)
4. አብራሪ «ሓ ሚም፤ አብራሪ በሆነ መፅሐፍ እንምላለን» (አድዱኻን፡ 1-2)
5. የአላህ ንግግር «ከአጋሪዎቹ መካከል የሆነ አንዱ ጥገኝነትን ቢጠይቅህ የአላህን ቃል ይሰማ ዘንድ አስጠጋው» (አት. ተውባህ፡ 6)
6. ብርሃን «ከጌታችሁ ዘንድ በእርግጥም አስረጅ መጣላችሁ። ወደ እናንተም ገለጭ የሆነን ብርሃን ቁርአን አወረድን» (የሴቶች ምእራፍ፡ 174)
7. መመሪያ «መፅሐፉንም ለሁሉም ነገር አብራሪ፤ መመሪያ እዝነትና ለሙስሊሞች አብሳሪ ሆኖ በአንተ ላይ አወረድነው» (አንነሕል፡ 89)
8. ብስራት «መፅሐፉንም ለሁሉም ነገር አብራሪ፤ መመሪያ እዝነትና ለሙስሊሞች አብሳሪ ሆኖ በአንተ ላይ አወረድነው።»
9. መድሐኒት «ከቁርአን ለምዕመናን ፍቱን መድሓኒትና እዝነት የሆነን እናወርዳለን በዳዮችም ኪሳራን እንጂ ሌላ አይጨመርላቸውም።» (አል እስራእ፡ 82)

10. መመከሪያ «እናንተ ሰዎች ሆይ! ከጌታችሁ ዘንድ ግሳጼ በደረቶች ውስጥም ላለው የመጠራጠር በሽታ ፍቱን መድህኒት፤ ለምዕመናንም ብርሃንና እዝነት የሆነ መልዕክት በእርግጥ መጣላችሁ።» (ዩኑስ፡ 57)
11. ጠንካራ ዘለበት «በአላህ የሚያምን ሰው ሁሉ የማትበጠስ ጠንካራ ገመድ ጨብጧል» (የላሟ፡ 256)
12. ሀኪም «ያሲን ጥበብ በተሞላበት ቁርኣን እምላሉ። አንተ በእርግጥ ከመልዕክተኞቹ መካከል አንዱ ነህ» (ያሲን፡ 1-2)
13. ተጠባባቂ «ከበፊቱ የነበረውን መፅሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ አደረግን» (የመዕዱ፡ 48)
14. የእምነት ብርቱ ገመድ «የእምነት ገመድም ሁላችሁም ያዙ። አትለያዩ።» (ኣሊ ዒምራን፡ 103)
15. ቀጥተኛ መንገድ «ይህ ቀጥተኛው መንገዴ ነው።» (የእስሳት ምእራፍ፡ 153)
16. ተደጋጋሚ «አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ ተደጋጋሚ የሆነን መፅሐፍ አወረደ (አዝዙመር፡ 23)
17. ተመሳሳይ «አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ ተደጋጋሚ የሆነን መፅሐፍ አወረደ፤» (አዝዙመር፡ 23)
18. የህይወት መንፈስ «ወደ አንተ ከትዕዛዛችን ሲሆን መንፈስን ቁርኣንን አወረድነው።» (አሽ. ሹራ፡ 52)
19. የላቀ «ቃፍ፤ በተከበረው ቁርኣን እምላለሁ በሙሐመድ አላመኑም።» (ቃፍ፡ 1)
20. ገሳጭ «ይህ ቁርኣን ለሰዎች ገሳጭና መድረስ ያለበት ነው።» (ኢብራሂም፡ 52)
21. አብሳሪ «አብሳሪና አስፈራሪ ሲሆን ተወረደ አብዛሀኞቻቸውም ተውት።» (ፉሲለት፡ 3-4)
22. የተወረደ «ዓለማት ጌታ የተወረደ።» (አል. ዋቂዓህ፡ 80)
23. የተከበረ «እርሱ የተከበረ ቁርኣን ነው።» (አል. ዋቂዓህ፡ 77)
24. የተባረከ «ይህ ያወረድነው ብሩክና ያንንም በፊት የነበረውን መፅሐፍ አረጋጋጭ ነው።» (የእስሳት ምዕራፍ፡ 92)
25. የበላይ «እርሱም በመፅሐፎች እናት ውስጥ እኛ ዘንድ እርግጥ ከፍተኛ ጥበብ የተሞላ ነው» (አል. ዙኹሩፍ፡ 4)
26. የተስተካከለ «ቀጥተኛ ሲሆን ከራሱ ዘንድ የሆነን ብርቱን ቅጣት ሊያስፈራራበት እነዚያንም በጎ ሰሪዎችን ለእነሱ መልካም ምንዳ ያላቸው መሆኑን ሊያበስርበት አወረደው።» (አልከህፍ፡ 2)
27. ራዕይ (ዜና ከዚያ እነርሱ በእሱ የተለያዩበት፤ የተወዛገቡበት በሆነው ከታላቁ ዜና ይጠያየቃሉ።) (ነበእ፡ 1-2)
28. እውቀት «እውቀት ከመጣልህ በኋላ በዒሳ የተከራከሩህን ሰዎች ኑ...» (ኣሊ ዒምራን፡ 61)
29. እውነት «ይህ ለዒሳ የነገርኩህ እውነተኛ ታሪክ ነው።» (ኣሊ ዒምራን፡ 62)
30. መሪ «ይህ ቁርኣን ወደ እዚያች እርሷ ቀጥተኛ ወደ ኾነችው መንገድ ይመራል።» (የለሊት ጉዞ፡9)
31. አስደናቂ «እኛ አስደናቂ የሆነን ቁርኣን ሰማን አሉ።» (አልጋኔን፡ 1)
32. ማስታወሻ «ስለዚህ የፈለገ ሰው ይገሰፅበታል።» (አል. ሙደሂር፡ 5) የሚሉት ከብዙ ጥቂቶቹ ናቸው።

ٱلَّذِى لَهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَلَمْ يَتَّخِذْ وَلَدًا وَلَمْ يَكُن لَّهُۥ شَرِيكٌ فِى ٱلْمُلْكِ
وَخَلَقَ كُلَّ شَىْءٍ فَقَدَّرَهُۥ تَقْدِيرًا ﴿٢﴾

**2.** አላህ ያ! የሰማያትና የምድር ንግስና የእርሱ ብቻ የሆነ ልጅንም ያልያዘ (ልጅም የሌለው) በንግስናውም ተጋሪ የሌለው ሁሉንም ነገር የፈጠረና በትክክልም (በስርአት) የመጠነ አምላክ ነው።

وَٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةً لَّا يَخْلُقُونَ شَيْـًٔا وَهُمْ يُخْلَقُونَ وَلَا يَمْلِكُونَ لِأَنفُسِهِمْ
ضَرًّا وَلَا نَفْعًا وَلَا يَمْلِكُونَ مَوْتًا وَلَا حَيَوٰةً وَلَا نُشُورًا ﴿٣﴾

**3.** ከሓዲያን ከእርሱ ከአላህ ሌላ ምንንም የማይፈጥሩንና እነርሱ ራሳቸው የሚፈጥሩ ለነፍሶቻቸውም (ከራሳቸው ላይ) ጉዳትን መከላከልም ሆነ ለራሳቸው ጥቅምን ማምጣት (ማስከበር) የማይችሉ ለሞት ማብቃትም ሆነ ህይወትን መለገስና ከሞት መቀስቀስንም የማይችሉን አማልዕክት አምላክ አድርገው ያዙ።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ إِنْ هَـٰذَآ إِلَّآ إِفْكٌ ٱفْتَرَىٰهُ وَأَعَانَهُۥ عَلَيْهِ قَوْمٌ ءَاخَرُونَ ۖ فَقَدْ جَآءُو
ظُلْمًا وَزُورًا ﴿٤﴾ وَقَالُوٓا۟ أَسَـٰطِيرُ ٱلْأَوَّلِينَ ٱكْتَتَبَهَا فَهِىَ تُمْلَىٰ عَلَيْهِ بُكْرَةً وَأَصِيلًا ﴿٥﴾ قُلْ
أَنزَلَهُ ٱلَّذِى يَعْلَمُ ٱلسِّرَّ فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ إِنَّهُۥ كَانَ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿٦﴾

**4-6.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ይህ ቁርኣን እርሱ (ሙሐመድ) በራሱ የቀጠፈውና በእርሱም ላይ ሌሎች ህዝቦች ያገዙት ውሸት እንጂ ሌላ አይደለም አሉ። በእርግጥም በደልንና እብለት ሰሩ (ፈፀሙ)። እነኚህ የመጀመሪያ ሰዎች ተረቶች (አፈታሪክ) ናቸው አሉ። አስፅፎታል፤ እናም በርሱ ላይ ጧትና ማታ ትነበብለታለች አሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለን ምስጢር የሚያውቀው አወረደው። እርሱ መሓሪና አዛኝ ነውና፣ በላቸው።

وَقَالُوا۟ مَالِ هَـٰذَا ٱلرَّسُولِ يَأْكُلُ ٱلطَّعَامَ وَيَمْشِى فِى ٱلْأَسْوَاقِ ۙ لَوْلَآ أُنزِلَ إِلَيْهِ مَلَكٌ فَيَكُونَ
مَعَهُۥ نَذِيرًا ﴿٧﴾ أَوْ يُلْقَىٰٓ إِلَيْهِ كَنزٌ أَوْ تَكُونُ لَهُۥ جَنَّةٌ يَأْكُلُ مِنْهَا ۚ وَقَالَ ٱلظَّـٰلِمُونَ إِن تَتَّبِعُونَ
إِلَّا رَجُلًا مَّسْحُورًا ﴿٨﴾ ٱنظُرْ كَيْفَ ضَرَبُوا۟ لَكَ ٱلْأَمْثَـٰلَ فَضَلُّوا۟ فَلَا يَسْتَطِيعُونَ سَبِيلًا ﴿٩﴾

**7-9.** ይህ መልዕክተኛ ምን አይነት መልዕክተኛ ነው? ምግብ የሚመገብ ወደ ገበያ የሚመላለስ፤ ከእርሱ ጋር አስፈራሪ ይሆን ዘንድ ወደ እርሱ መልአክ (በገሃድ) ለምን አይወርድም ኖሯልን? አሉ። ወይም ወደ እርሱ ድልብ አይሰጠውምን? ወይም ከእርሷ የሚበላት አትክልት ለእርሱ አትኖረውምን? አሉ። በዳዮችም ላመኑት የተደገመበትን ሰው እንጂ ሌላን አትከተሉም አሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለአንተ ምሳሌዎችን እንዴት እንዳደረጉልህና ከዚያ እንዴት እንደ ተሳሳቱ ተመልከት። ወደ እውነት ለመድረስ መንገድንም አይችሉም።

تَبَارَكَ ٱلَّذِيٓ إِن شَآءَ جَعَلَ لَكَ خَيۡرٗا مِّن ذَٰلِكَ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ وَيَجۡعَل لَّكَ قُصُورَۢا ﴿١٠﴾ بَلۡ كَذَّبُواْ بِٱلسَّاعَةِۖ وَأَعۡتَدۡنَا لِمَن كَذَّبَ بِٱلسَّاعَةِ سَعِيرًا ﴿١١﴾ إِذَا رَأَتۡهُم مِّن مَّكَانِۢ بَعِيدٖ سَمِعُواْ لَهَا تَغَيُّظٗا وَزَفِيرٗا ﴿١٢﴾ وَإِذَآ أُلۡقُواْ مِنۡهَا مَكَانٗا ضَيِّقٗا مُّقَرَّنِينَ دَعَوۡاْ هُنَالِكَ ثُبُورٗا ﴿١٣﴾ لَّا تَدۡعُواْ ٱلۡيَوۡمَ ثُبُورٗا وَٰحِدٗا وَٱدۡعُواْ ثُبُورٗا كَثِيرٗا ﴿١٤﴾ قُلۡ أَذَٰلِكَ خَيۡرٌ أَمۡ جَنَّةُ ٱلۡخُلۡدِ ٱلَّتِي وُعِدَ ٱلۡمُتَّقُونَۚ كَانَتۡ لَهُمۡ جَزَآءٗ وَمَصِيرٗا ﴿١٥﴾ لَّهُمۡ فِيهَا مَا يَشَآءُونَ خَٰلِدِينَۚ كَانَ عَلَىٰ رَبِّكَ وَعۡدٗا مَّسۡـُٔولٗا ﴿١٦﴾

**10-16.** ያ፣ ቢሻ ከዚህ ካሉት የተሻለን ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው አትክልቶችን የሚያደርግልህ ህንጻ ቤቶችንም ላንተ ሚያደርግልህ የሚያደርግልህ ጌታ ችሮታው በዛ። (ክብሩ ሰፋ) ይልቁንም እነርሱ በትንሳኤ አስተባበሉ። በትንሳኤ ላስተባበለም ሰው ሁሉ አቃጣይ እሳት አዘጋጅተናል። ከሩቅ ስፍራ ባየቻቸው ጊዜ የእርሷን የቁጭት መገንፈልንና ማናፋትን ይሰማሉ። ከጓደኞቻቸው ጋር (ከሰይጣኖቻቸው ጋር) በአንድ የታሰሩ ሆነውም ከእርሷ በጠባብ ስፍራ በተጣሉ ጊዜ በዚያ ስፍራ ጥፋትን ይጠራሉ። (ዋ! ጥፋታችን ይላሉ)። ዛሬማ አንድን ጥፋት ብቻ አትጥሩ። ይልቁንም ብዙን ጥፋት ጥሩ (ይባላሉ)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (እንዲህ) በላቸው ይህ የተሻለ ነውን? ወይስ ጥንቁቆቹ ተስፋ የተሰጡት የዘልዓለሟ ገነት? ገነት ለእነርሱ ምንዳና መመለሻ ሆነች። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ሆነው የሚፈልጉት ሁሉ አለላቸው። ይህ ተስፋ ከጌታህ ሊለመን የሚገባው ተስፋ ነው።

وَيَوْمَ يَحْشُرُهُمْ وَمَا يَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ فَيَقُولُ ءَأَنتُمْ أَضْلَلْتُمْ عِبَادِى هَٰٓؤُلَآءِ أَمْ هُمْ
ضَلُّوا۟ ٱلسَّبِيلَ ﴿١٧﴾ قَالُوا۟ سُبْحَٰنَكَ مَا كَانَ يَنۢبَغِى لَنَآ أَن نَّتَّخِذَ مِن دُونِكَ مِنْ أَوْلِيَآءَ
وَلَٰكِن مَّتَّعْتَهُمْ وَءَابَآءَهُمْ حَتَّىٰ نَسُوا۟ ٱلذِّكْرَ وَكَانُوا۟ قَوْمًۢا بُورًا ﴿١٨﴾ فَقَدْ كَذَّبُوكُم بِمَا
تَقُولُونَ فَمَا تَسْتَطِيعُونَ صَرْفًا وَلَا نَصْرًا ۚ وَمَن يَظْلِم مِّنكُمْ نُذِقْهُ عَذَابًا كَبِيرًا ﴿١٩﴾

**17-19.** እነርሱንና ከአላህ ሌላ የሚገዟቸውን*[1] የሚሰበስብበትንና እናንተ እነዚህን ባሮቼን አሳሳታችሁን? ወይስ እነርሱው እራሳቸው መንገድን ሳቱ? የሚልበትን ቀን (አስታውስ)። ተመላኪዎች*[2] ጥራት ይገባህ። ከአንተ ሌላ ረዳቶችን ልንይዝ አይገባንም። ግን እነርሱንም ሆነ አባቶቻቸውን መገንዘብን እስከ ተውና ጠፊ ህዝቦችም እስከሚሆኑ ድረስ አጣቀምካቸው፤ ይላሉ። በምትሉትም አማልክቶቻችሁ አስዋሹዋችሁ። ቅጣቴን መገፍተርንም ሆነ እራሳችሁን መርዳት አትችሉም። ከናንተም የሚበድልን ሰው ታላቅን ቅጣት እናቀምሰዋለን። (ይባላሉ)።

*1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ)፡- «ሙዓዝ ሆይ! በሰዎች ላይ ያለውን የአላህ ሐቅ ታውቃለህን?». አሉ። እኔም «አላህና መልዕክተኛው በደንብ ያውቃሉ» አልኳቸው። እሳቸውም «እሱን ብቻ እንዲያመልኩና ከእርሱ ጋር ሌላን እንዳያመልኩ ነው። በርሱ ላይ ያሉትን ሐቆች ታውቃለህን?» አሉ። እኔም «አላህና መልዕክተኛው በደንብ ያውቃሉ» አልኳቸው። እሳቸውም «መልካም ከሰሩ ላይቀጣቸው ነው» አሉ።

*2 ይህ አባባል ነብዩ ዒሳ፤ ዑዘይር፤ መላኮችና ጋኔኖች ማለት (ወይም ጣኦትን ብቻ) የተመለከውን አካል ሁሉንም የሚል ክርክር ያለ ሲሆን የሚመረጠውም ሁሉንም ማጠቃለሉ ነው። ዝንጉ ብሎ ይህ አንቀፅ ከመተርጎም ተው ማለቱ የተመረጠ ነው።

እንደዚሁም ዚክር ማለት ቁርአን ወይም ነብያት ያስተማሩት ነገር ወይም የአላህ ፀጋዎችን ማመስገን የሚሉትን ማለት ነው የሚሉም አሉ። የሚመረጠው ግን ነብያት ያስተማሩት ነገር ማለት ነው የሚለውን ነው። ነብዩ ዒሳ፤ ዑዘይር፤ መላኮችና ጋኔኖች ማለት (ወይም ጣኡታትን ብቻ) የተመለከውን አካል ሁሉንም የሚል ክርክር ያለ ሲሆን የሚመረጠውም ሁሉንም ማጠቃለሉ ነው።

እውነትን ከውሸት የመለየት ከ (7-16) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ከሓዲያን ነብዩን (ﷺ) በድህነታቸው እና «እንደማንኛውም ተራ ግለሰብ ገበያ ለገበያ የሚዘዋወሩ» እያሉ በማነወራቸው ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَمَآ أَرْسَلْنَا قَبْلَكَ مِنَ ٱلْمُرْسَلِينَ إِلَّآ إِنَّهُمْ لَيَأْكُلُونَ ٱلطَّعَامَ وَيَمْشُونَ فِى ٱلْأَسْوَاقِ ۗ
وَجَعَلْنَا بَعْضَكُمْ لِبَعْضٍ فِتْنَةً أَتَصْبِرُونَ ۗ وَكَانَ رَبُّكَ بَصِيرًا ﴿٢٠﴾

**20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊትም ከመልዕክተኞች እነርሱ በእርግጥ ምግብን የሚበሉ በገበያዎችም የሚሄዱ ሆነው እንጂ አላክንም። ከፊላችሁንም ለከፊሉ ፈተና አድርገናል። ትታገሳላችሁን? ጌታህም ተመልካች ነው።

**እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-20) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ጌትነቱን የሚያሳዩ ክንውኖችን በገሃድ ማየት፤
2. ማጋራትንና አጋሪዎችን ማውገዝ ማጣጣል፤
3. ተውሒድን፤ ሙቶ መነሳትንና ነብይነት በይፋ ማረጋገጥን
4. ከሓዲያን የተውሒድን ጥሪ በምን መልኩ እንደተቃወሙት፤
5. የወህይን እውነተኝነትና የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማፅደቅና ማረጋገጥ፤
6. አጋሪዎች የተውሂዱን ጥሪ ሲመለከቱ ያላቸውን የደከመ አመላካከት እንዲሁም ለማደናቀፍ የወሰዱት ሙከራ ሁሉ መክሸፉ;
7. የአብዛኞች ከሓዲያን የክህደት ምክንያት ሙቶ መነሳትን አለመቀበል ስለ መሆኑ፤
8. አላህን መፍራትና ትልቅነቱን ማረጋገጥ፤
9. ተመላኪዎች ስለ አምላኪዎቻቸው ሲጠየቁ የሚከሰተው ጭንቀት፤
10. መላኢኮች፤ ነብያቶችና ትላልቅ ሰዎች ከአምላኪዎቻቸው የአምልኮ ተግባር ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌላቸውና ራሳቸው ነፃ እንደሚያደርጉ፤
11. ከሀብት ጋር የእድሜ መርዘም ሊያስከትለው የሚችለው አደጋ፤
12. ይህች ዓለም የፈተና ሀገር መሆንዋን እንማራለን።

ይህን ቃል የሚናገረው አካል መላኢኮች ወይም የራሳቸው የከሓዲያን ናቸው በሚል ክርክር አለበት የሚመረጠው ግን የራሳቸው የከሓዲያን ነገር ነው የሚለዉን ነው።

۞ وَقَالَ ٱلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ لِقَآءَنَا لَوۡلَآ أُنزِلَ عَلَيۡنَا ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ أَوۡ نَرَىٰ رَبَّنَاۗ لَقَدِ ٱسۡتَكۡبَرُواْ
فِيٓ أَنفُسِهِمۡ وَعَتَوۡ عُتُوّٗا كَبِيرٗا ﴿٢١﴾ يَوۡمَ يَرَوۡنَ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ لَا بُشۡرَىٰ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُجۡرِمِينَ
وَيَقُولُونَ حِجۡرٗا مَّحۡجُورٗا ﴿٢٢﴾ وَقَدِمۡنَآ إِلَىٰ مَا عَمِلُواْ مِنۡ عَمَلٖ فَجَعَلۡنَٰهُ هَبَآءٗ مَّنثُورًا ﴿٢٣﴾

**21-23.** እነዚያ መገናኘታችንን የማይፈሩ ሰዎች በእኛ ላይ ለምን መላእክት አልወረደም ወይም ጌታችንን ለምን አናይም? አሉ። በነፍሶቻቸው ውስጥ በእርግጥ ኮሩ። ታላቅንም አመፅ አመፁ። መላዕክትን በሚያዩበት ቀን በዚያ ጊዜ ለአመፀኞች የምስራች የላቸውም። የተከለከለ ክልክልም አድርገን ይላሉ። ወደ ሰሩት ስራም እናስባለን። ከዚያ እንደ ተበተነ ትቢያ እናደርገዋለን።*

✷ አቡዳዉድ እንደዘገቡት (ዓሲ ኢብኑ ዋኢል የተባለ ከሃዲ ሲሞት መቶ ባሪያዎችን ነፃ አውጡልኝ ብሎ ስለ ነበር ሒሸ የተባለው አንዱ ልጁ ሀምሳ ነፃ ካደረገ በኋላ ሁለተኛው ልጅ ዐምር ብኑል ዓሲ ይህን ተግባር ከመፈፀሜ በፊት ነቢዩን መጠየቅ ይኖርብኛል በሚል ወደ ነቢዩ ሂደው ሲጠይቁ (ሙስሊም በነበረ ኖሮ ነፃ ብታወጡለት ብተሰድቁለት ብትሐጅጁለት ይጠቅመው ነበር) በማለት ከሓዲያን በአኺራ ምንም ኸይረ እንደማይጠቅማቸው ያስተምራሉ።

أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِ يَوۡمَئِذٍ خَيۡرٞ مُّسۡتَقَرّٗا وَأَحۡسَنُ مَقِيلٗا ﴿٢٤﴾ وَيَوۡمَ تَشَقَّقُ ٱلسَّمَآءُ بِٱلۡغَمَٰمِ وَنُزِّلَ
ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ تَنزِيلًا ﴿٢٥﴾ ٱلۡمُلۡكُ يَوۡمَئِذٍ ٱلۡحَقُّ لِلرَّحۡمَٰنِۚ وَكَانَ يَوۡمًا عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ عَسِيرٗا ﴿٢٦﴾

**24-26.** የገነት ሰዎች በዚያ ቀን በመርጊያ የተሻሉ በማረፊያም በጣም ያማሩ ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰማይ በደመና የምትቀደድበትንና መላእክት መውረድን የሚወርዱበትን ቀን (አስታውስ)። እውነተኛው ንግስና በዚያ ቀን ለአልረህማን ብቻ ነው። በከሓዲያን ላይ አስቸጋሪ ቀን ነው።

وَيَوْمَ يَعَضُّ ٱلظَّالِمُ عَلَىٰ يَدَيْهِ يَقُولُ يَٰلَيْتَنِى ٱتَّخَذْتُ مَعَ ٱلرَّسُولِ سَبِيلًا ﴿٢٧﴾
يَٰوَيْلَتَىٰ لَيْتَنِى لَمْ أَتَّخِذْ فُلَانًا خَلِيلًا ﴿٢٨﴾ لَّقَدْ أَضَلَّنِى عَنِ ٱلذِّكْرِ بَعْدَ إِذْ جَآءَنِى
وَكَانَ ٱلشَّيْطَٰنُ لِلْإِنسَٰنِ خَذُولًا ﴿٢٩﴾

**27-29.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዳይም ከመልዕክተኛው ጋር ቀጥተኛን መንገድ ምነው ይዤ በሆነ ዋ ምኞቴ! እያለ በፀፀት ሁለት እጆችን የሚነክስበትን ቀን (አስታውስ)። ዋ፣ ጥፋቴ፣ እገሌን ወዳጅ ባልያዝኩ ኖሮ እመኛለሁ። የእምነት ቃል✴ የሆነው ቁርኣን ከመጣልኝ በኋላ ከማስታወስ በእርግጥ አሳሳተኝ ይላል። ሰይጣንም ለሰው አጋላጭ ነው።

✴ ቁርኣን ወይም ነብዩ ወይም ጠቃሚ ምክር ወይም እምነት ማለት ነው ተብሏል። የተመረጠው ግን ቁርኣን የሚለው ነው። ይህ አረፍተ ነገር አላህ የሰይጣንን ተንኮል ለመግለፅ የተናገረው ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ ከከሃዲው ንግግሮች ተጨማሪ ነው ይላሉ። የተመረጠው ግን የአላህ ቃል የሚለው ነው።

እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ ከ (27-29) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ዑቅበህ ኢብኑ አቡ ሙዓይጥ ኢስላምን ተቀብሎ ሳለ ወዳጁ ኡመያህ ኸለፍ ወይም ኡበይ ኢብኑኸለፍ ስለ ሰደበውና ለሱ ሲል ክዶ ነብዩን በማውገዙ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَقَالَ ٱلرَّسُولُ يَٰرَبِّ إِنَّ قَوْمِى ٱتَّخَذُوا۟ هَٰذَا ٱلْقُرْءَانَ مَهْجُورًا ﴿٣٠﴾ وَكَذَٰلِكَ جَعَلْنَا لِكُلِّ نَبِىٍّ
عَدُوًّا مِّنَ ٱلْمُجْرِمِينَ ۗ وَكَفَىٰ بِرَبِّكَ هَادِيًا وَنَصِيرًا ﴿٣١﴾

**30-31.** መልዕክተኛውም (ሙሐመድ) ጌታዬ ሆይ፣ ህዝቦቼ ይህንን ቁርኣን የተተወ ነገር አደረጉት አለ። እንደዚሁም ለነብዩ ሁሉ ከአመፀኞች የሆነ ጠላትን አድርገናል። መሪነትና ረዳትነት በጌታህ በቃ።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَوْلَا نُزِّلَ عَلَيْهِ ٱلْقُرْءَانُ جُمْلَةً وَٰحِدَةً ۚ
كَذَٰلِكَ لِنُثَبِّتَ بِهِۦ فُؤَادَكَ ۖ وَرَتَّلْنَٰهُ تَرْتِيلًا ﴿٣٢﴾

**32.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ቁርኣን በእርሱ ላይ ለምን በጠቅላላ በአንድ ጊዜ አልተወረደለትም አሉ። ልክ እንደዚሁ በእርሱ ልብህን ልናረጋ (ከፋፍለን በተለያየ አወረድነው)። ቀስ በቀስ መለያየትንም ለየነው።

**እውነት ከውሸት የመለየት ምዕራፍ ከአንቀፅ (21-32) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የመካ ከሓዲያን የነበራቸው ኲራትና ትዕቢት ምን ይመስል እንደነበር፤
2. መላኢኮች ሩህን በሚመዙበት ጊዜ የቂያማ ቀን ማየት እንዳለ፤
3. አመፀኞችን ከልክሎ ምእመናን ማብሰር፤
4. የአጋሪዎች ተግባር ፋይዳ ቢስ ስለ መሆኑ፤
5. የሙዕሚኖች ሂሳብ በግማሽ ቀን እንደሚያበቃ
6. የሙቶ መነሳትን ህቀኝነት ማረጋገጥ፤
7. ቁርአን ችላ ብለው ለተውት ሰዎች የነብዩ ምክርነትና ወደ አላህ የሚያቀርቡት ክስ፤
8. ማንኛውም አስተማሪ ጠላት እንዳለው፤
9. ቁርአን ቀስ በቀስ የወረደበት ምክንያት፤
10. አመፀኞችና ግፈኞች በፊታቸው ወደ ጀሀነም እንደሚቀሰቀሱ

وَلَا يَأْتُونَكَ بِمَثَلٍ إِلَّا جِئْنَٰكَ بِٱلْحَقِّ وَأَحْسَنَ تَفْسِيرًا ﴿٣٣﴾

**33.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በየትኛውም ጥያቄ አይመጡብህም እውነተኛውን መልስና መልካም ፍችም የምናመጣልህ ብንሆን እንጅ።

ٱلَّذِينَ يُحْشَرُونَ عَلَىٰ وُجُوهِهِمْ إِلَىٰ جَهَنَّمَ أُوْلَٰٓئِكَ شَرٌّ مَّكَانًا وَأَضَلُّ سَبِيلًا ﴿٣٤﴾

**34.** እነዚያ በፊቶቻቸው ላይ እየተጎተቱ ወደ ገሀነም የሚሰበሰቡ ናቸው። እነዚያ ስፍራቸው የከፋ መንገዳቸውም የጠመመ ናቸው።

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ وَجَعَلْنَا مَعَهُۥٓ أَخَاهُ هَٰرُونَ وَزِيرًا ﴿٣٥﴾ فَقُلْنَا ٱذْهَبَآ إِلَى
ٱلْقَوْمِ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا فَدَمَّرْنَٰهُمْ تَدْمِيرًا ﴿٣٦﴾ وَقَوْمَ نُوحٍ لَّمَّا كَذَّبُوا۟ ٱلرُّسُلَ أَغْرَقْنَٰهُمْ
وَجَعَلْنَٰهُمْ لِلنَّاسِ ءَايَةً ۖ وَأَعْتَدْنَا لِلظَّٰلِمِينَ عَذَابًا أَلِيمًا ﴿٣٧﴾

**35-37.** በእርግጥም ለሙሳ መጽሐፍን ሰጠነው። ከእርሱም ጋር ወንድሙን ሃሩንን ረዳት አደረግንለት። ወደ እነዚያም በተዐምራቶቻችን ወደ አስተባበሉት ህዝቦች ሂዱ አልናቸው። (አስዋሿቸውም) ማጥፋትንም አጠፋናቸው። የኑህን ሰዎችም መልዕክተኞችን ባስተባበሉ ጊዜ አሰመጥናቸው። ለሰዎችም መገሰጫ አደረግናቸው፤ ለበደለኞችም አሳማሚን ቅጣት አዘጋጅተናል።

وَعَادًا وَثَمُودَا۟ وَأَصْحَٰبَ ٱلرَّسِّ وَقُرُونًۢا بَيْنَ ذَٰلِكَ كَثِيرًا ﴿٣٨﴾ وَكُلًّا ضَرَبْنَا لَهُ ٱلْأَمْثَٰلَ ۖ
وَكُلًّا تَبَّرْنَا تَتْبِيرًا ﴿٣٩﴾ وَلَقَدْ أَتَوْا۟ عَلَى ٱلْقَرْيَةِ ٱلَّتِىٓ أُمْطِرَتْ مَطَرَ ٱلسَّوْءِ ۚ أَفَلَمْ يَكُونُوا۟
يَرَوْنَهَا ۚ بَلْ كَانُوا۟ لَا يَرْجُونَ نُشُورًا ﴿٤٠﴾

**38-40.** ዓድንም፣ ሰሙድንም፣ የረስ ሰዎችንና በዚህ መካከል የነበሩትንም ብዙ የክፍለ ዘመናት* ህዝቦች (አጠፋን።) ሁሉንም ገሠጽን። ለእነርሱ ምሳሌዎችን ገለጽን። ሁሉንም ማጥፋትን አጠፋናቸውም። በዚያችም ክፉ ዝናብን በተዘነበችው ከተማ ላይ (የመካ ከሓዲያን) በእርግጥ መጥተዋል። የሚያዩዋት አልነበሩምን? በእውነት መቀስቀስን የማይፈሩ ነበሩ።

* እነዚህ ክፍለ ዘመናት የተባሉትን ህዝቦች ማንነት ከመወሰን አኳያ ብዙ የተወራ ቢሆንም በኢብራሂም (9) ኛው አንቀፅ ላይ እንደገለፀው ሁሉ ከኑህ፣ ከዓድና ከሰሙድ ህዝቦች በኋላ ከረስ ህዝቦች በፊት የነበሩትን ህዝቦች ማለት ነው የሚለው የተመረጠው ነው።

وَإِذَا رَأَوْكَ إِن يَتَّخِذُونَكَ إِلَّا هُزُوًا أَهَٰذَا ٱلَّذِى بَعَثَ ٱللَّهُ رَسُولًا ﴿٤١﴾ إِن كَادَ لَيُضِلُّنَا عَنْ
ءَالِهَتِنَا لَوْلَآ أَن صَبَرْنَا عَلَيْهَا ۚ وَسَوْفَ يَعْلَمُونَ حِينَ يَرَوْنَ ٱلْعَذَابَ مَنْ أَضَلُّ سَبِيلًا ﴿٤٢﴾

**41-42.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባዩህ ጊዜ ያ፣ አላህ መልዕክተኛ አድርጎ የላከው ይህ ነውን? እያሉ መሳለቂያ እንጂ ሌላ አያደርጉህም። እነሆ በእርሷ ላይ መታገሳችን ፅናታችን ባልነበረ ኖሮ ከአማልክቶቻችን ሊያሳስተን ቀርቦ ነበር ሲሉም ይሳለቃሉ። ወደ ፊትም ቅጣትን በሚያዩ ጊዜ መንገድን የተሳሳተ ማን እንደ ሆነ በእርግጥ ያውቃሉ።

أَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ أَفَأَنتَ تَكُونُ عَلَيْهِ وَكِيلًا ﴿٤٣﴾ أَمْ تَحْسَبُ أَنَّ أَكْثَرَهُمْ
يَسْمَعُونَ أَوْ يَعْقِلُونَ ۚ إِنْ هُمْ إِلَّا كَٱلْأَنْعَٰمِ بَلْ هُمْ أَضَلُّ سَبِيلًا ﴿٤٤﴾

**43-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ፍላጎቱን አምላክ አድርጎ የያዘን ሰው አየህን? አንተም በእርሱ ላይ ጠባቂ ትሆናለህን? ይልቁንም አብዛኛዎቻቸው የሚሰሙ ወይም የሚያውቁ መሆናቸውን ታስባለህን? እነርሱ እንደ እንስሳዎች እንጂ ሌላ አይደሉም። ከቶውንም እነርሱ ከእንስሳዎች ይልቅ መንገድን የተሳሳቱ ናቸው።

أَلَمْ تَرَ إِلَىٰ رَبِّكَ كَيْفَ مَدَّ ٱلظِّلَّ وَلَوْ شَآءَ لَجَعَلَهُۥ سَاكِنًا ثُمَّ جَعَلْنَا ٱلشَّمْسَ عَلَيْهِ
دَلِيلًا ﴿٤٥﴾ ثُمَّ قَبَضْنَٰهُ إِلَيْنَا قَبْضًا يَسِيرًا ﴿٤٦﴾ وَهُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ لِبَاسًا وَٱلنَّوْمَ
سُبَاتًا وَجَعَلَ ٱلنَّهَارَ نُشُورًا ﴿٤٧﴾ وَهُوَ ٱلَّذِىٓ أَرْسَلَ ٱلرِّيَٰحَ بُشْرًۢا بَيْنَ يَدَىْ رَحْمَتِهِۦ ۚ وَأَنزَلْنَا
مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً طَهُورًا ﴿٤٨﴾ لِّنُحْـِۧىَ بِهِۦ بَلْدَةً مَّيْتًا وَنُسْقِيَهُۥ مِمَّا خَلَقْنَآ أَنْعَٰمًا وَأَنَاسِىَّ
كَثِيرًا ﴿٤٩﴾ وَلَقَدْ صَرَّفْنَٰهُ بَيْنَهُمْ لِيَذَّكَّرُوا۟ فَأَبَىٰٓ أَكْثَرُ ٱلنَّاسِ إِلَّا كُفُورًا ﴿٥٠﴾

**45-50.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ጥላን እንዴት እንደ ዘረጋ አላየህምን? በሻ ኖሮ የረጋ ባደረገው ነበር። ከዚያ ፀሐይን በእርሱ ላይ ለጥላው ምልክት አደረግን። ከዚያ ቀስ በቀስ ወደ እኛ ሰበሰብነው። እርሱም ያ! ለእናንተ ሌሊትን ልብስ እንቅልፍንም ማረፊያ ያደረገ። ቀንንም መበተኛ ያደረገላችሁ አምላክ ነው። (አላህ) እርሱ ያ! ንፋሶችን አብሳሪዎች ሲሆን ከዝናቡ በስተፊት የላከ ነው። ከሰማይ አጥሪ ውሃን አወረድን። በእርሱ የሞተችን አገር ህያው ልናደርግበት ከፈጠርነውም ፍጡር እንስሳዎችንና ብዙ ሰዎችንም ልናጠጣው አወረድነው። ፀጋችንን ይገነዘቡም ዘንድ በመካከላቸው ከፋፈልነው* አበላለጥነዉም። ግን አብዛሀኞዎቹ ሰዎች ክህደትን እንጂ እንቢ አሉ።

* ለሰይጣንና ለሰራዊቶቹ ረዳት ነው ማለቱ የተመረጠ በመሆኑ ነው ይህን የመርጥኩት እንጂ። ለከሓዲያን ረዳት ነው ለአምላኩ አሸናፊ ነው ማለት ሊሆን ይችላል ያሉም አሉ።

وَلَوْ شِئْنَا لَبَعَثْنَا فِي كُلِّ قَرْيَةٍ نَّذِيرًا ﴿٥١﴾ فَلَا تُطِعِ ٱلْكَٰفِرِينَ وَجَٰهِدْهُم بِهِۦ جِهَادًا كَبِيرًا ﴿٥٢﴾

**51-52.** በሻን ኖሮ በየከተማይቱ አስፈራሪን በላክን ነበር። ከሓዲያንን አትታዘዛቸው። በእርሱም በቁርኣን ታላቅን ትግል ታገላቸው።

۞ وَهُوَ ٱلَّذِى مَرَجَ ٱلْبَحْرَيْنِ هَٰذَا عَذْبٌ فُرَاتٌ وَهَٰذَا مِلْحٌ أُجَاجٌ
وَجَعَلَ بَيْنَهُمَا بَرْزَخًا وَحِجْرًا مَّحْجُورًا ﴿٥٣﴾ وَهُوَ ٱلَّذِى خَلَقَ مِنَ ٱلْمَآءِ بَشَرًا
فَجَعَلَهُۥ نَسَبًا وَصِهْرًا ۗ وَكَانَ رَبُّكَ قَدِيرًا ﴿٥٤﴾

**53-54.** እርሱ ያ ሁለትን ባህሮች አጎራብቶ የለቀቀ ነው። አንዱ ጥም የሚቆርጥና ጣፋጭ ነው። ሌላኛው ደግሞ የሚመረግግ ጨው ነው። በመካከላቸውም ከመቀላቀል መለያንና የተከለለን ክልል ያደረገ ነው። እርሱም ያ! ከውሃ ሰውን የፈጠረ የዝምድናና የአማችም ባለቤት ያደረገው ነው። ጌታህ ሁሉን ነገር ቻይ ነው።

وَيَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَا لَا يَنفَعُهُمْ وَلَا يَضُرُّهُمْ ۗ وَكَانَ ٱلْكَافِرُ عَلَىٰ رَبِّهِۦ ظَهِيرًا ﴿٥٥﴾

**55.** ከአላህ ሌላ የማይጠቅማቸውንና የማይጎዳቸውን አካል ይገዛሉ። ከሓዲ በጌታው ላይ (በማመፅ ለሰይጣን) ረዳት ነው።

وَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ إِلَّا مُبَشِّرٗا وَنَذِيرٗا ٥٦ قُلۡ مَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍ إِلَّا مَن شَآءَ أَن
يَتَّخِذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ سَبِيلٗا ٥٧ وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡحَيِّ ٱلَّذِي لَا يَمُوتُ وَسَبِّحۡ بِحَمۡدِهِۦۚ وَكَفَىٰ بِهِۦ
بِذُنُوبِ عِبَادِهِۦ خَبِيرًا ٥٨ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَا فِي سِتَّةِ أَيَّامٖ ثُمَّ
ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ ٱلرَّحۡمَٰنُ فَسۡـَٔلۡ بِهِۦ خَبِيرٗا ٥٩ وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱسۡجُدُواْۤ لِلرَّحۡمَٰنِ قَالُواْ
وَمَا ٱلرَّحۡمَٰنُ أَنَسۡجُدُ لِمَا تَأۡمُرُنَا وَزَادَهُمۡ نُفُورٗا۩ ٦٠

**56-60.** አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን እንጂ አላክንህም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርሱ ላይ ዋጋን በፍፁም አልጠይቃችሁም። ግን ወደ ጌታው መልካም መንገድን ለመያዝ የሻ ሰው ይስራ በላቸው። በዚያም በማይሞተው ህያው አምላክ ላይ ተመካ ከማመስገንም ጋር አጥራው። የባሮቹን ኃጢአቶች ውስጥ በማወቅ በእርሱ በቃ። ያ! ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ። ከዚያ በዐርሹ ላይ ከፍ አለ። አልረህማን ነው። ከእርሱም ዐዋቂን ጠይቅ። ለእነርሱም ለአልረህማን ስገዱ። በተባሉ ጊዜ አልረህማን ማን ነው? ለምታዘንና ለማናውቀው እንስግዳለን? ይላሉ። ይህ መራቅንም ጨመራቸው።

**እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ ከአንቀፅ (33-56) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ህዝቦቹን ካስጠነቀቀ በኋላ እንደሚያጠፋ፤
2. የአስተባባዩች መጨረሻ ምን ያህል የከፋ እንደሆነ፤
3. ቁረይሾች ነብዩን (ﷺ) ያስተባበሉበት ምክንያት ምን እንደነበር፤
4. በዳዕዋ ምክንያት ነብዩ (ﷺ) ያጋጥማቸው የነበረው ስቃይ፤
5. የተሳሳተ ሰው እውነት እንደሚያውቅ መስሎ ይኖርና ቅጣቱን ሲያይ እንደሚያምን
6. የሰው ልጅ ስሜቱን እስካልተከተለ ድረስ ወደ ቀናው መንገድ መመራት እንደሚችል
7. ስለ አላህ አንድነትና ብቸኛ አምላክነት ማስረጃዎችን መደርደር፤
8. በነብዩ (ﷺ) ዘመን ሌላ ነብይ እንዳልነበር መጠቆም፤
9. ከሓዲያንን በዲን ጉዳይ መታዘዝ ክልክል ስለመሆኑ፤
10. ከሓዲያንን በማስረጃ መዋጋት የጂሃድ አካል ስለመሆኑ፤
11. የአላህን እውቀት ስፋት የችሎታ ግዝፈት የሚያሳዩ ክንውኖች፤
12. የሰይጣን አጋር የሆኑትን አጋሪዎች ማውገዝ፤
13. ንፁህ ውሃ ማለት ምን እንደሆነ መጠቆም፤

እዚህ ላይ «ከፋፈልነው» የተባለው ነገር ምን እንደ ሆነ ለመወሰን ብዙ ክርክሮች የተደረጉበት ቢሆንም የተሻለውና የተመረጠው ቁርአንን ማለቱ ነው።

تَبَارَكَ ٱلَّذِى جَعَلَ فِى ٱلسَّمَآءِ بُرُوجًا وَجَعَلَ فِيهَا سِرَٰجًا وَقَمَرًا مُّنِيرًا ﴿٦١﴾ وَهُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ
ٱلَّيْلَ وَٱلنَّهَارَ خِلْفَةً لِّمَنْ أَرَادَ أَن يَذَّكَّرَ أَوْ أَرَادَ شُكُورًا ﴿٦٢﴾

**61-62.** ያ፣ በሰማይ ቡሩጆችን ያደረገና በእርሷም አንፀባራቂን ፀሐይ አብሪ ጨረቃንም የፈጠረ ጌታ ክብሩ በጣም ላቀ። እርሱም ያ! ያመለጠውን ስራ ማስታወስን ለሚፈልግ ወይም ማመስገንን ለሚፈልግ ሰው ሌሊትንና ቀንን ተተካኪ ያደረገ ነው።

وَعِبَادُ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلَّذِينَ يَمْشُونَ عَلَى ٱلْأَرْضِ هَوْنًا وَإِذَا خَاطَبَهُمُ ٱلْجَٰهِلُونَ قَالُوا۟ سَلَٰمًا ﴿٦٣﴾
وَٱلَّذِينَ يَبِيتُونَ لِرَبِّهِمْ سُجَّدًا وَقِيَٰمًا ﴿٦٤﴾ وَٱلَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱصْرِفْ عَنَّا عَذَابَ جَهَنَّمَ ۖ
إِنَّ عَذَابَهَا كَانَ غَرَامًا ﴿٦٥﴾ إِنَّهَا سَآءَتْ مُسْتَقَرًّا وَمُقَامًا ﴿٦٦﴾ وَٱلَّذِينَ إِذَآ أَنفَقُوا۟ لَمْ يُسْرِفُوا۟
وَلَمْ يَقْتُرُوا۟ وَكَانَ بَيْنَ ذَٰلِكَ قَوَامًا ﴿٦٧﴾ وَٱلَّذِينَ لَا يَدْعُونَ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ وَلَا يَقْتُلُونَ
ٱلنَّفْسَ ٱلَّتِى حَرَّمَ ٱللَّهُ إِلَّا بِٱلْحَقِّ وَلَا يَزْنُونَ ۚ وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ يَلْقَ أَثَامًا ﴿٦٨﴾ يُضَٰعَفْ لَهُ
ٱلْعَذَابُ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ وَيَخْلُدْ فِيهِۦ مُهَانًا ﴿٦٩﴾ إِلَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ عَمَلًا صَٰلِحًا
فَأُو۟لَٰٓئِكَ يُبَدِّلُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِهِمْ حَسَنَٰتٍ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿٧٠﴾

**63-70.** የአልረህማን ባሮች እነዚያ በምድር ላይ በዝግታ የሚሄዱት ባለጌዎች (በክፉ) ባነጋገሯቸው ጊዜ ሰላም የሚሉት ናቸው። እነዚያም ለጌታቸው በግንባራቸው ተደፊዎችና ቋሚዎች ሆነው የሚያድሩት ሰዎች ናቸው። እነዚያም ጌታችን ሆይ፣ የገሀነምን ቅጣት ከእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የማያልቅ ነውና። የሚሉት ናቸው። እርሷ መርጊያና መቀመጫ በመሆን ከፋች! የሚሉ ናቸው። እነዚያም በለገሱ ጊዜ የማያባክኑት የማይቆጥቡትም ናቸው። በዚህም መካከል ልግስናቸው ትክክለኛ የሆነ ነው። እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይገዙ፤[*1] ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ህግ የማይገድሉ[*2] እና የማያመነዝሩት ናቸው። ይህንን የሚፈፅም ሰው ወንጀለኛ ይሆናል። በትንሳኤ ቀን ቅጣት ለእርሱ ይደራረብበታል። በእርሱ ውስጥም የተዋረደ ሆኖ ይኖራል። ተፀፅቶ የተመለሰና ያመነ መልካምንም የሰራ ሰው ብቻ ሲቀር እነዚያም አላህ መጥፎ ስራዎቻቸውን በመልካም ስራዎች ይለውጣል። አላህም እጅግ መሓሪና አዛኝ ነው።[*3]

✶1 አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) «ከሰባት አጥፊ ወንጀሎች ታቀቡ» በማለት ተናገሩ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እነርሱ እናማን ናቸው?» የሚል ጥያቄ ቀረበላቸው። «በአላህ ማጋራት፤ ድግምት፤ አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ አግባብ መግደል፤ አራጣ መብላት፤ የየቲምን ገንዘብ መብላት በአላህ መንገድ በሚደረግ ጦርነት ላይ መሸሽ እና ንፁሐን አማኝ እንስቶችን በዝሙት ስማቸውን ማጥፋት» ሲሉ መለሱ።

✶2 ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልእክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «እያንዳንዱ ሙስሊም ለሌላው ሙስሊም ደሙም፤ ክብሩም ገንዘቡም እርም ነው።»

✶3 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ)፡- «ብዙ ነፍስ ያጠፉ፤ ዝሙትን በብዛት የፈፀሙ፤ ጣኦት አምላኪያን ወደ አላህ መልዕክተኛ መጡና «ሙሐመድ ሆይ! ይህ የምትናገረውና ሰዎችን የምትጠራበት ነገር መልካም ነውና ወንጀሎቻችንን የምናሰርዝበትን ብትነግረን አሏቸው። ይህን ጊዜም «እነዚያም ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የማይገዙት፤ ያችንም አላህ እርም ያደረጋትን ነፍስ ያለ ሕግ የማይገድሉት የማያመነዝሩትም ናቸው።» (አልፉርቃን፡ 68) እና «በላቸው፡- እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ! ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ» (አዝዙመር፡ 53) የሚለው የቁርኣን አንቀፅ ወረደ።

وَمَن تَابَ وَعَمِلَ صَٰلِحٗا فَإِنَّهُۥ يَتُوبُ إِلَى ٱللَّهِ مَتَابٗا ٧١ وَٱلَّذِينَ لَا يَشۡهَدُونَ ٱلزُّورَ
وَإِذَا مَرُّواْ بِٱللَّغۡوِ مَرُّواْ كِرَامٗا ٧٢ وَٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِّرُواْ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمۡ لَمۡ يَخِرُّواْ عَلَيۡهَا صُمّٗا
وَعُمۡيَانٗا ٧٣ وَٱلَّذِينَ يَقُولُونَ رَبَّنَا هَبۡ لَنَا مِنۡ أَزۡوَٰجِنَا وَذُرِّيَّٰتِنَا قُرَّةَ أَعۡيُنٖ وَٱجۡعَلۡنَا
لِلۡمُتَّقِينَ إِمَامًا ٧٤ أُوْلَٰٓئِكَ يُجۡزَوۡنَ ٱلۡغُرۡفَةَ بِمَا صَبَرُواْ وَيُلَقَّوۡنَ فِيهَا تَحِيَّةٗ وَسَلَٰمًا ٧٥
خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ حَسُنَتۡ مُسۡتَقَرّٗا وَمُقَامٗا ٧٦

**71-76.** ተፀጽቶ የተመለሰና መልካምን ተግባር የሰራ ሰው እርሱ በአላህ ዘንድ የተወደደን መመለስ ይመለሳል። እነዚያ በሐሰት የማይመሰክሩ በውድቅ ቃልም ተናጋሪ አጠገብ ባለፉ ጊዜ የተከበሩ ሆነው የሚያልፉ ናቸው። እነዚያ በጌታቸው አንቀፆች በተገሠፁ ጊዜ የተረዱ ተቀባዮች ሆነው እንጂ ደንቆሮዎችና እውሮች ሆነው በእርሷ ላይ የማይደፉባት ናቸው። እነዚያ ጌታችን ሆይ! ከሚስቶቻችንና ከዘሮቻችን ለዓይኖች መርጊያን ለእኛ ስጠን አላህን ለሚፈሩትም መሪ አድርገን የሚሉ ናቸው። እነዚያ በመታገሳቸው የገነትን ሰገነቶች ይመነዳሉ። በእርሷም ውስጥ ውዳሴንና ሰላምታን ይሰጣሉ። በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ሆነው (ይሰጣሉ)። መርጊያና መኖሪያይቱ ጀነት አማረች።

እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ ከ (68-71) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሙሽሪኮች በሽርክ ጊዜ ብዙ ወንጀሎችን በመስራታቸው ለነብዩ (ﷺ) መጥተው «የምታስተምረው ነገር በጣም ጥሩ ነበር። ከሠራነው ወንጀል መፍትሄ ብትነግረን ኖሮ ስላሏቸው ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ዋሂዲ እና ሱዩጢ)

قُلْ مَا يَعْبَؤُاْ بِكُمْ رَبِّى لَوْلَا دُعَآؤُكُمْ فَقَدْ كَذَّبْتُمْ فَسَوْفَ يَكُونُ لِزَامًا ﴿٧٧﴾

77. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ፀሎታችሁ ባልነበረ ኖሮ ጌታዬ እናንተን ከምንም አይቆጥራችሁም ነበር። በእርግጥም አስተባበላችሁ። እናም ወደ ፊት ቅጣት ይይዛችሁ ይሆናል በላቸው።

**እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ ከአንቀፅ (57-77) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. በዳዕዋ ስም ደመወዝ መጠየቅ እንደማይገባ፤
2. በአላህ ላይ መመካት ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. የአላህ ባሪያዎች ያላቸው ባህሪያት፤
4. ራስን ዝቅ ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ፤
5. መጥፎን ነገርን በመልካም መመለስ ያለው ምንዳ፤
6. የሌሊት ሶላትና የገሀነምን እሳት መስጋት ያለው ምንዳ፤
7. ገንዘብን በመስጠት መካከለኛ መሆን ያለው ምንዳ፤
8. ሽርክ፤ ነፍስ ማጥፋት፤ ዝሙት ክልክል መሆናቸውንና የወንጀሎች ሁሉ ዋና መሆናቸውን፤
9. ተውባ ያለፈን ወንጀል እንደምታስምርና ተውበት ለማድረግ ነፍስ ጉሮሮ እስካልደረሰች ድረስ አጋጣሚው እንዳለ ስለመሆኑ
10. የሀሰት ምስክርነት ክልክል ስለመሆኑ፤
11. አስፈላጊ ካልሆኑ ነገሮች ራስን ማሸሽ ያለው ምንዳ፤
12. ቁርአንን በጥሞና ማንበብና መልዕክቱን መመርመር በምክሮቹ መመከርና በመመሪያዎቹ መመራት ታላቅ ምንዳ እንዳለው፤
13. የሰው ልጅ አላህን ካልተገዛ ከእንሰሳ ሁሉ በታች እንደሚሆን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ እውነትን ከውሸት የመለየት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (26)
# የባለቅኔዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አሽሹዐራእ)

سُورَةُ الشُّعَرَاءِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (227) ናቸው።
### የሱረቱ አሽ-ሹዓራ መግቢያ

በመግቢያው ላይ ስለ ቁርኣን ትልቅነት ያወሳል። በማስከተልም አላህ በከሀዲያን ላይ ቅጣትን ማውረድ የሚችል መሆኑን በመግለፅ ከሀዲያን በሚያደርጉት መጥፎ ድርጊት እንዳይበሳጩ ያለፉትን ነብያት ታሪክ በማስታወስ ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) ያፅናናል። ሙሳና ሀሩንን ከፊርአውን ጋር ያሳለፉትን ትግል፤ ነብዩ ኢብራሂም፤ ኑህ፤ ሁድ፤ ሷሊህን፤ ሉጥና ሹዐይብ ከተላኩላቸው ሰዎች ጋር ያሳለፉትን ታሪክ በዝርዝር ያወሳል። በተጨማሪም የእነዚያ ሰባት ነብያት ጥሪና አስተምህሮት መሰረቱ አንድ መሆኑን፣ ከሓዲያንም ለነብያት የሚሰጡት መልስ ተመሳሳይ መሆኑን በይፋ ያውጃል። በመጨረሻም እንዳጀማመሩ ሁሉ ቁርኣንን በማሞገስና ነብዩ ሙሐመድም (ﷺ) ከገጣሚዎች እንዳልሆኑ፤ ቁርኣንም ግጥም እንደማይባል በማስተማር መልዕክቱን ያጠቃልላል።

አሁን በምትለው አምላክ ከሃዲ ሆነህ ወይም በእኔ ጌትነት ማለትም ሊሆን ይችላል። የረሳሁኝ ሁኜ፤ ለሞት ያበቃል ብዬ ሳልገምት ማለት ሊሆንም ይቻላል። ወይም ነብይነት ወይም ጠቃሚ ትምህርት ማለት ነው በሚል ልዩነቶች አሉ። የተመረጠው ግን ጠቃሚ ትምህርት ማለት ነው የሚለው ነው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

طسٓمٓ ۝١ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡمُبِينِ ۝٢

**1-2.** ጧ፣ ሲን፣ ሚይም።* እነዚህ ግልጽ የሆነው መጽሀፍ አንቀፆች ናቸው።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በነኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

لَعَلَّكَ بَٰخِعٞ نَّفۡسَكَ أَلَّا يَكُونُواْ مُؤۡمِنِينَ ۝٣ إِن نَّشَأۡ نُنَزِّلۡ عَلَيۡهِم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ ءَايَةٗ
فَظَلَّتۡ أَعۡنَٰقُهُمۡ لَهَا خَٰضِعِينَ ۝٤ وَمَا يَأۡتِيهِم مِّن ذِكۡرٖ مِّنَ ٱلرَّحۡمَٰنِ مُحۡدَثٍ إِلَّا كَانُواْ عَنۡهُ
مُعۡرِضِينَ ۝٥ فَقَدۡ كَذَّبُواْ فَسَيَأۡتِيهِمۡ أَنۢبَٰٓؤُاْ مَا كَانُواْ بِهِۦ يَسۡتَهۡزِءُونَ ۝٦

**3-6.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲዎች አማኞች ባለ መሆናቸው በቁጭት ነፍስህን እንዳታጠፋ ይፈራልሃል (ያሰጋል)። ብንሻ ኖሮ በእነርሱ ላይ ከሰማይ ተዐምርን እናወርድና አንገቶቻቸው ለእርሷ ተዋራጆች እናደርጋለን። ከአልረህማን ዘንድ አዲስ የተወረደ ቁርኣን አይመጣላቸውም። ከእርሱ የሚሸሹ ቢሆኑ እንጂ። በእርግጥም አስተባበሉ። የዚያም በርሱ ይሳለቁበት የነበሩት ወሬዎች ፍጻሜ ይመጣባቸዋል።

أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَى ٱلۡأَرۡضِ كَمۡ أَنۢبَتۡنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوۡجٖ كَرِيمٍ ۝٧ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ
أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ۝٨ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ۝٩

**7-9.** ወደ ምድርም በውስጧ ከመልካም በቃይ ጎሳ ሁሉ ብዙን እንዳበቀልን አላዩምን በዚህ አስደናቂ ምልክት አለበት አብዛኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም። ጌታህ በትክክል አሸናፊ፤ አዛኝ ነው።

وَإِذۡ نَادَىٰ رَبُّكَ مُوسَىٰٓ أَنِ ٱئۡتِ ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ۝١٠ قَوۡمَ فِرۡعَوۡنَۚ أَلَا يَتَّقُونَ ۝١١ قَالَ رَبِّ
إِنِّيٓ أَخَافُ أَن يُكَذِّبُونِ ۝١٢ وَيَضِيقُ صَدۡرِي وَلَا يَنطَلِقُ لِسَانِي فَأَرۡسِلۡ إِلَىٰ هَٰرُونَ ۝١٣
وَلَهُمۡ عَلَيَّ ذَنۢبٞ فَأَخَافُ أَن يَقۡتُلُونِ ۝١٤

**10-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ሙሳን ወደ እነዚያ በደለኛ ህዝቦች ወደ ፈርዖን ህዝቦች ሂድ አላህን አይፈሩምን? በማለት በጠራው ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ሙሳም ጌታዬ ሆይ እኔ ያስተባብሉኛል ብዬ እፈራለሁ። ልቤም ይጠባል ምላሴም እንደልቡ መናገር አይችልም። ስለዚህ ወደ ሃሩን ላክ። በተጨማሪም ለእነርሱ በእኔ ላይ (የደም) ወንጀል አላቸው። ስለዚህ እንዳይገድሉኝም እፈራለሁ አለ።

قَالَ كَلَّاۖ فَٱذۡهَبَا بِـَٔايَٰتِنَآۖ إِنَّا مَعَكُم مُّسۡتَمِعُونَ ﴿١٥﴾ فَأۡتِيَا فِرۡعَوۡنَ فَقُولَآ إِنَّا رَسُولُ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٦﴾ أَنۡ أَرۡسِلۡ مَعَنَا بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ﴿١٧﴾

**15-17.** አላህ አለ ተው። አይነኩህም ሁለታችሁም በተአምሮቻችን ታጅባችሁ ሂዱ። እኛ ከናንተ ጋር ሁነን ሰሚዎች ነንና። ወደ ፈርዖንም ሂዱና። በሉትም እኛ የዓለማት ጌታ መልዕክተኞች ነን በሉት። የኢስራኤልን ልጆችም ልቀቅልን።

قَالَ أَلَمۡ نُرَبِّكَ فِينَا وَلِيدٗا وَلَبِثۡتَ فِينَا مِنۡ عُمُرِكَ سِنِينَ ﴿١٨﴾ وَفَعَلۡتَ فَعۡلَتَكَ ٱلَّتِي فَعَلۡتَ وَأَنتَ مِنَ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿١٩﴾ قَالَ فَعَلۡتُهَآ إِذٗا وَأَنَا۠ مِنَ ٱلضَّآلِّينَ ﴿٢٠﴾ فَفَرَرۡتُ مِنكُمۡ لَمَّا خِفۡتُكُمۡ فَوَهَبَ لِي رَبِّي حُكۡمٗا وَجَعَلَنِي مِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿٢١﴾ وَتِلۡكَ نِعۡمَةٞ تَمُنُّهَا عَلَيَّ أَنۡ عَبَّدتَّ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ﴿٢٢﴾

**18-22.** ፈርዖንም፡ ልጅ ሆንህ በእኛ ውስጥ አላሳደግንህምን? በእኛ ውስጥም ከዕድሜህ ብዙ ዓመታትን አልተቀመጥክምን? አለ። ያችን የሰራሃትን ስራህን አልሰራህምን? አንተ ከውለታ ቢሶች ነህ (አለ)። ሙሳም አለ፡ ያን ጊዜ እኔም ከተሳሳቱት ሆኜ ሰራኋት። በፈራኋችሁ ጊዜ ከናንተ ሸሸሁ። ጌታዬም ለእኔ ጥበብን ሰጠኝ። ከመልዕክተኞችም አደረገኝ። ይህችም የኢስራኤልን ልጆች ባሪያ በማድረግህ በእኔ ላይ የምትመጻድቅባት ፀጋ ናት።

قَالَ فِرۡعَوۡنُ وَمَا رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٢٣﴾ قَالَ رَبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَآۖ إِن كُنتُم مُّوقِنِينَ ﴿٢٤﴾ قَالَ لِمَنۡ حَوۡلَهُۥٓ أَلَا تَسۡتَمِعُونَ ﴿٢٥﴾ قَالَ رَبُّكُمۡ وَرَبُّ ءَابَآئِكُمُ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٢٦﴾ قَالَ إِنَّ رَسُولَكُمُ ٱلَّذِيٓ أُرۡسِلَ إِلَيۡكُمۡ لَمَجۡنُونٞ ﴿٢٧﴾

**23-27.** ፈርዖን ሙሳ ሆይ! ላከኝ የምትለው የዓለማት ጌታ ምንድ ነው? አለ። ሙሳ፡- የሰማያት የምድርና በመካከላቸውም ያለው ፍጡር ሁሉ ጌታ ነው።

የምታረጋግጡ ብትሆኑ ነገሩ ይህ ነው አለው። ፈርዖንም፡- ዙሪያውን ላሉት ሰዎች አትሰሙምን? አለ። ሙሳ፡- ጌታችሁና የመጀመሪያዎች አባቶቻችሁም ጌታ ነው አለ። ፈርዖን፡- ያ ወደ እናንተ የተላከው መልዕክተኛችሁ በእርግጥ ዕብድ ነው አለ።

قَالَ رَبُّ ٱلۡمَشۡرِقِ وَٱلۡمَغۡرِبِ وَمَا بَيۡنَهُمَآۖ إِن كُنتُمۡ تَعۡقِلُونَ ﴿٢٨﴾ قَالَ لَئِنِ ٱتَّخَذۡتَ إِلَٰهًا غَيۡرِي لَأَجۡعَلَنَّكَ مِنَ ٱلۡمَسۡجُونِينَ ﴿٢٩﴾ قَالَ أَوَلَوۡ جِئۡتُكَ بِشَيۡءٖ مُّبِينٖ ﴿٣٠﴾ قَالَ فَأۡتِ بِهِۦٓ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴿٣١﴾

**28-31.** ሙሳ፡- የእናንተ የምስራቅና የምእራብ በመካከላቸውም ያለው ነገር ሁሉ ጌታ ነው። ታውቁ እንደሆናችሁ እመኑበት አለ። ፈርዖን ከእኔ ሌላ አምላክን ብትይዝ በእውነቱ ከእስረኞቹ አደርግሃለሁ አለ። ሙሳ፡- ግልጽ የሆነ አስረጅ ባመጣህም እንኳን? አለው። ፈርዓውን እንግዲያውስ ከእውነተኞች እንደሆንክ አስረጁን አምጣ አለ።

**ከባለቅኔዎች ከአንቀፅ ምዕራፍ (1-31) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቁርኣንን ተዓምርነትና መሰሉን ሊያመጡ እንደማይችሉ በግልፅ መጋበዝ፤
2. ነብዩ (ﷺ) ያጋጠማቸው ሀዘንና ጭንቀት ምን ይመስል እንደነበር፤
3. ተገዶ የሚመጣ እምነት ስለማይጠቅም አላህ እንዳላስገደደ፤
4. በአላህ አናቅፅ ላይ የሚያስተባብሉ ሰዎችን ከሚጠብቃቸው መጥፎ ነገሮች ማስጠንቀቅ፤
5. መሬትን በውሃ ህያው በማድረጉና ልዩ ልዩ ቡቃያዎችን በማብቀሉ የሙቶ መነሳትን ሀቅነት እንደሚያስረዳ፤
6. ነፍስ ማጥፋት በሁሉም ሰው ዘንድ የተወገዘ ስለመሆኑ፤
7. ውለታን ላላስታወሱ ሰዎች ያለመመፃደቅ ማስታወስ እንደማይቻል፤
8. በሀገሩ ውስጥ ፍትህ አላገኙሁም ያለ ሰው አገሩን ለቆ መሸሽ እንደሚችል፤
9. የአላህ ጌትነት ማረጋገጥ፤
10. የውሸት ባለቤቶች ሲከራከሩ ለመርታት ብለው እንደሚዋሹ፤
11. ካፊሮችም ሆኑ ትዕቢተኞች በማስረጃ መርታት ሲያቅታቸው በጉልበት እንደሚያስፈራሩ እንማራለን።

فَأَلۡقَىٰ عَصَاهُ فَإِذَا هِيَ ثُعۡبَانٞ مُّبِينٞ ﴿٣٢﴾ وَنَزَعَ يَدَهُۥ فَإِذَا هِيَ بَيۡضَآءُ لِلنَّٰظِرِينَ ﴿٣٣﴾

**32-33.** በትሩንም ጣለ። እርሷም ወዲያውኑ ግልጽ እባብ ሆነች። እጁንም አወጣ እርሷም ወዲያውኑ ለተመልካቾች ነጭ (የምታበራ) ሆነች።

قَالَ لِلْمَلَإِ حَوْلَهُۥٓ إِنَّ هَٰذَا لَسَٰحِرٌ عَلِيمٌ ﴿٣٤﴾ يُرِيدُ أَن يُخْرِجَكُم مِّنْ أَرْضِكُم بِسِحْرِهِۦ فَمَاذَا تَأْمُرُونَ ﴿٣٥﴾

**34-35.** ፈርዖን በዙሪያው ላሉት መማክርት ይህ በእርግጥ ዐዋቂ ድግምተኛ ነው አለ። ከምድራችሁ በድግምት ሊያወጣችሁ ይፈልጋልና ምንን ታዛላችሁ? አላቸው።

قَالُوٓا۟ أَرْجِهْ وَأَخَاهُ وَٱبْعَثْ فِى ٱلْمَدَآئِنِ حَٰشِرِينَ ﴿٣٦﴾ يَأْتُوكَ بِكُلِّ سَحَّارٍ عَلِيمٍ ﴿٣٧﴾

**36-37.** አሉት እርሱን ወንድሙንም አቆይና በየከተሞቹ ሰብሳቢዎችን ላክ በጣም ዐዋቂ ድግምተኞችን ሁሉ ያመጡልሃልና።

فَجُمِعَ ٱلسَّحَرَةُ لِمِيقَٰتِ يَوْمٍ مَّعْلُومٍ ﴿٣٨﴾ وَقِيلَ لِلنَّاسِ هَلْ أَنتُم مُّجْتَمِعُونَ ﴿٣٩﴾ لَعَلَّنَا نَتَّبِعُ ٱلسَّحَرَةَ إِن كَانُوا۟ هُمُ ٱلْغَٰلِبِينَ ﴿٤٠﴾ فَلَمَّا جَآءَ ٱلسَّحَرَةُ قَالُوا۟ لِفِرْعَوْنَ أَئِنَّ لَنَا لَأَجْرًا إِن كُنَّا نَحْنُ ٱلْغَٰلِبِينَ ﴿٤١﴾ قَالَ نَعَمْ وَإِنَّكُمْ إِذًا لَّمِنَ ٱلْمُقَرَّبِينَ ﴿٤٢﴾

**38-42.** ድግምተኞችም በታወቀ ቀን ቀጠሮ ተሰበሰቡ። ለሰዎቹም እናንተ ተሰብስባችኋልን? ተባለ። ድግምተኞችን እነርሱ አሸናፊዎች ቢሆኑ እንከተል ዘንድ (ተባለ)። ድግምተኞቹ በመጡ ጊዜ ለፈርዖን እኛ አሸናፊዎች ብንሆን ለእኛ ዋጋ አለን? አሉት። አዎን እናንተም ያን ጊዜ ከባለሟሎቹ ትሆናላችሁ አላቸው።

قَالَ لَهُم مُّوسَىٰٓ أَلْقُوا۟ مَآ أَنتُم مُّلْقُونَ ﴿٤٣﴾ فَأَلْقَوْا۟ حِبَالَهُمْ وَعِصِيَّهُمْ وَقَالُوا۟ بِعِزَّةِ فِرْعَوْنَ إِنَّا لَنَحْنُ ٱلْغَٰلِبُونَ ﴿٤٤﴾ فَأَلْقَىٰ مُوسَىٰ عَصَاهُ فَإِذَا هِىَ تَلْقَفُ مَا يَأْفِكُونَ ﴿٤٥﴾ فَأُلْقِىَ ٱلسَّحَرَةُ سَٰجِدِينَ ﴿٤٦﴾ قَالُوٓا۟ ءَامَنَّا بِرَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٤٧﴾ رَبِّ مُوسَىٰ وَهَٰرُونَ ﴿٤٨﴾

**43-48.** ሙሳ ለእነርሱ እናንተ የምትጥሉትን ጣሉ አላቸው። ገመዶቻቸውንና በትሮቻቸውንም ጣሉ። በፈርዖንም ክብር ይሁንብን። እኛ በእርግጥ አሸናፊዎቹ እኛ ነን አሉ። ሙሳ ብትሩን ጣለ። ወዲያውም እርሷ የሚያስመስሉትን ሁሉ ትውጣለች። ድግምተኞችም ሰጋጆች ሆነው ወደቁ። እነርሱም አሉ፡- በዓለማት ጌታ አመንን። በሙሳና በሃሩን ጌታ።

قَالَ ءَامَنتُمْ لَهُۥ قَبْلَ أَنْ ءَاذَنَ لَكُمْ ۖ إِنَّهُۥ لَكَبِيرُكُمُ ٱلَّذِى عَلَّمَكُمُ ٱلسِّحْرَ فَلَسَوْفَ تَعْلَمُونَ ۚ لَأُقَطِّعَنَّ أَيْدِيَكُمْ وَأَرْجُلَكُم مِّنْ خِلَٰفٍ وَلَأُصَلِّبَنَّكُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٤٩﴾

**49.** (ፈርዖንም) ለእናንተ ሳልፈቅድላችሁ በፊት ለእርሱ አመናችሁን? እርሱ ያ ድግምትን ያስተማራችሁ ታላቃችሁ ነው። ወደፊትም የሚያገኛችሁን በእርግጥ ታውቃላችሁ እጆቻችሁንና እግሮቻችሁን (ቀኝና ግራን) በማናጋት እቆራርጣችኋለሁ። ሁላችሁንም እሰቅላችሁ አለሁ አለ።

قَالُوا۟ لَا ضَيْرَ ۖ إِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا مُنقَلِبُونَ ﴿٥٠﴾ إِنَّا نَطْمَعُ أَن يَغْفِرَ لَنَا رَبُّنَا خَطَٰيَٰنَآ أَن كُنَّآ أَوَّلَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٥١﴾

**50-51.** (እነርሱም) አሉ፡- ጉዳት የለብንም እኛ ወደ ጌታችን ተመላሾች ነን። እኛ የምዕምናን መጀመሪያ በመሆናችን ጌታችን ኃጢአቶቻችንን ለኛ ሊምር እንከጅላለን።

۞ وَأَوْحَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنْ أَسْرِ بِعِبَادِىٓ إِنَّكُم مُّتَّبَعُونَ ﴿٥٢﴾ فَأَرْسَلَ فِرْعَوْنُ فِى ٱلْمَدَآئِنِ حَٰشِرِينَ ﴿٥٣﴾ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَشِرْذِمَةٌ قَلِيلُونَ ﴿٥٤﴾ وَإِنَّهُمْ لَنَا لَغَآئِظُونَ ﴿٥٥﴾ وَإِنَّا لَجَمِيعٌ حَٰذِرُونَ ﴿٥٦﴾ فَأَخْرَجْنَٰهُم مِّن جَنَّٰتٍ وَعُيُونٍ ﴿٥٧﴾ وَكُنُوزٍ وَمَقَامٍ كَرِيمٍ ﴿٥٨﴾ كَذَٰلِكَ ۖ وَأَوْرَثْنَٰهَا بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ ﴿٥٩﴾

**52-59.** ወደ ሙሳም ባሮቼን ይዘህ ሌሊት ሂድ እናንተ የሚከተሏችሁ ናችሁና ስንል ላክን። ፈርዖንም በየከተሞቹ ሰብሳቢዎችን እንዲህ ሲል ላከ። እነዚህ ጥቂቶቹ ጭፍሮች ናቸው። እነርሱም ለእኛ አስቆጪዎች ናቸው። እኛም ብዙዎች ጥንቁቆች ነን አለ። አወጣናቸውም፤ ከአትክልቶችና ከምንጮች። ከድልቦችም ከመልካም መቀመጫዎችም እንደዚሁ ለኢስራኤል ልጆች አወረስናትም።

فَأَتْبَعُوهُم مُّشْرِقِينَ ﴿٦٠﴾ فَلَمَّا تَرَٰٓءَا ٱلْجَمْعَانِ قَالَ أَصْحَٰبُ مُوسَىٰٓ إِنَّا لَمُدْرَكُونَ ﴿٦١﴾ قَالَ كَلَّآ ۖ إِنَّ مَعِىَ رَبِّى سَيَهْدِينِ ﴿٦٢﴾

**60-62.** ፀሐይዋ ስትወጣም ተከተሏቸው። ሁለቱ ጭፍሮችም በተያዩ ጊዜ የሙሳ ጓዶች እኛ (የፈርዖን ሰዎች) የሚደርሱብን ነን አሉ። ሙሳ ተው ተው! ጌታዬ ከእኔ ጋር ነው። በእርግጥ ይመራኛል አለ።

**ከባለቅኔዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (32-60) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. ለነብያት ተዓምራቶችን እንደሰጠ ማረጋገጥ፤
2. አስተዳዳሪ ወይም ኃላፊ አሳሳቢ በሆኑ ነገሮች ላይ አማካሪዎቹን ማማከር እንዳለበት፤
3. ድግምት ከእውቀት ዘርፎች አንዱ መሆኑንና መማሩም ሆነ ማስተማሩ ክልክል ስለ መሆኑ፤
4. በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ለሚወዳደሩ ሽልማቶችን መስጠት፤
5. በእውቀት ለሚሰሩ ስራዎችና ለሚደረጉ ውድድሮች መሽቀዳደም ጠቃሜታ እንዳለው፤
6. ፊርዓውን ከድግምተኞች ጋር ያደረገው ሙከራ የከሸፈ አካሄድ እንደነበርና አላህ ለነብያት ተዓምራትን እንደሰጠ ማረጋገጥ፤
7. የእምነት ጥንካሬ የጀግንነት ምንጭ ስለመሆኑ፤
8. በአላህ ላይ ተስፋን ማሳመር ተገቢ ስለመሆኑ፤
9. ብሔራዊ ዘመቻ ማወጅ ተገቢ ስለመሆኑ፤
10. አላህ ግፈኞችንና አባካኞችን እንደሚያጠፋ እንማራለን።

فَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰ مُوسَىٰٓ أَنِ ٱضۡرِب بِّعَصَاكَ ٱلۡبَحۡرَۖ فَٱنفَلَقَ فَكَانَ كُلُّ فِرۡقٖ كَٱلطَّوۡدِ ٱلۡعَظِيمِ ٦٣
وَأَزۡلَفۡنَا ثَمَّ ٱلۡأٓخَرِينَ ٦٤ وَأَنجَيۡنَا مُوسَىٰ وَمَن مَّعَهُۥٓ أَجۡمَعِينَ ٦٥ ثُمَّ أَغۡرَقۡنَا ٱلۡأٓخَرِينَ ٦٦
إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ٦٧ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ٦٨

**63-68.** ወደ ሙሳም ባህሩን በበትርህ ምታው ስንል ላክንበት። ከዚያ መታውና ተከፈለ፤ ክፍሉም ሁሉ እንደ ታላቅ ጋራ ሆነ። እዚያም ዘንድ ሌሎችን አቀረብን። ሙሳንና ከእርሱ ጋር ያሉትን ሰዎች ሁሉንም አዳን። ከዚያ ሌሎቹን አሰመጥን። በዚህ ውስጥ ታላቅ ተዐምር አለበት አብዛሀኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም። ጌታህ አላህ እርሱ አሸናፊና አዛኝ ነው።

وَٱتۡلُ عَلَيۡهِمۡ نَبَأَ إِبۡرَٰهِيمَ ٦٩ إِذۡ قَالَ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦ مَا تَعۡبُدُونَ ٧٠ قَالُواْ نَعۡبُدُ
أَصۡنَامٗا فَنَظَلُّ لَهَا عَٰكِفِينَ ٧١ قَالَ هَلۡ يَسۡمَعُونَكُمۡ إِذۡ تَدۡعُونَ ٧٢ أَوۡ يَنفَعُونَكُمۡ
أَوۡ يَضُرُّونَ ٧٣ قَالُواْ بَلۡ وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا كَذَٰلِكَ يَفۡعَلُونَ ٧٤ قَالَ أَفَرَءَيۡتُم مَّا كُنتُمۡ
تَعۡبُدُونَ ٧٥ أَنتُمۡ وَءَابَآؤُكُمُ ٱلۡأَقۡدَمُونَ ٧٦ فَإِنَّهُمۡ عَدُوّٞ لِّيٓ إِلَّا رَبَّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٧٧ ٱلَّذِي
خَلَقَنِي فَهُوَ يَهۡدِينِ ٧٨ وَٱلَّذِي هُوَ يُطۡعِمُنِي وَيَسۡقِينِ ٧٩ وَإِذَا مَرِضۡتُ فَهُوَ يَشۡفِينِ ٨٠
وَٱلَّذِي يُمِيتُنِي ثُمَّ يُحۡيِينِ ٨١ وَٱلَّذِيٓ أَطۡمَعُ أَن يَغۡفِرَ لِي خَطِيٓـَٔتِي يَوۡمَ ٱلدِّينِ ٨٢

**69-82.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእነርሱም በህዝቦችህ ላይ የኢብራሂምን ወሬ አንብብላቸው። ለአባቱና ለህዝቦቹ ምንን ትገዛላችሁ

ባለ ጊዜ። ጣኦታትን እንገዛለን። እርሷንም በመገዛት ላይ እንቆያለን አሉ። (ኢብራሂም) አለ፡- በጠራችኋቸው ጊዜ ይሰሟችኋልን? ወይስ ይጠቅሟችኋልን? ወይስ ይጎዷችኋልን? የለም ነገር ግን አባቶቻችን እንደዚሁ ሲሰሩ አገኘንና (እኛም እነርሱን እንከተላለን) አሉት። ትገዙት የነበራችሁትን አስተዋላችሁን? እናንተም የቀድሞዎቹ አባቶቻችሁም እየተገዛችሁት ያለው። እነርሱም ጣኦቶችም ለእኔ ጠላቶች ናቸው። የዓለማት ጌታ ብቻ ሲቀር እርሱ ወዳጄ ነው። እርሱ ያ! የፈጠረኝ ነው። እርሱም ይመራኛል። ያም እርሱ የሚያበላኝና የሚያጠጣኝ ነው። በታመምኩም ጊዜ እርሱ ያሽረኛል። ያም የሚገድለኝ ከዚያ ህያው የሚያደርገኝ ነው። ያም በፍርዱ ቀን ኃጢአቴን ሊምርልኝ የምከጅለው ነው።

رَبِّ هَبۡ لِي حُكۡمٗا وَأَلۡحِقۡنِي بِٱلصَّٰلِحِينَ ٨٣ وَٱجۡعَل لِّي لِسَانَ صِدۡقٖ فِي ٱلۡأٓخِرِينَ ٨٤ وَٱجۡعَلۡنِي مِن وَرَثَةِ جَنَّةِ ٱلنَّعِيمِ ٨٥ وَٱغۡفِرۡ لِأَبِيٓ إِنَّهُۥ كَانَ مِنَ ٱلضَّآلِّينَ ٨٦ وَلَا تُخۡزِنِي يَوۡمَ يُبۡعَثُونَ ٨٧

**83-87.** (ኢብራሂምም) ጌታዬ ሆይ፣ እውቀትን ስጠኝ በደጋጎቹም ሰዎች አስጠጋኝ። በኋለኞችም ህዝቦች ውስጥ ለእኔ መልካም ዝናን አድርግልኝ። የፀጋይቱን ገነት ከሚወርሱትም ሰዎች አድርገኝ። ለአባቴም ኃጢያቱን ማር እርሱ ከተሳሳቱት ነበርና።

يَوۡمَ لَا يَنفَعُ مَالٞ وَلَا بَنُونَ ٨٨ إِلَّا مَنۡ أَتَى ٱللَّهَ بِقَلۡبٖ سَلِيمٖ ٨٩ وَأُزۡلِفَتِ ٱلۡجَنَّةُ لِلۡمُتَّقِينَ ٩٠ وَبُرِّزَتِ ٱلۡجَحِيمُ لِلۡغَاوِينَ ٩١ وَقِيلَ لَهُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡ تَعۡبُدُونَ ٩٢ مِن دُونِ ٱللَّهِ هَلۡ يَنصُرُونَكُمۡ أَوۡ يَنتَصِرُونَ ٩٣ فَكُبۡكِبُواْ فِيهَا هُمۡ وَٱلۡغَاوُۥنَ ٩٤ وَجُنُودُ إِبۡلِيسَ أَجۡمَعُونَ ٩٥

**88-95.** በሚቀሰቀሱበት ቀንም አታዋርደኝ። ገንዘብም ሆነ ልጆች በማይጠቅሙበት ቀን፣ ወደ አላህ በንፁህ ልብ የመጣ ሰው ቢሆን አንጂ። ገነትም ለፈሪዎች በምትቀረብበት ቀን፣ ገሀነምም ለጠማሞች በምትገለፅበት ቀን። ለእነርሱም በሚባል ቀን እነዚያ ከአላህ ሌላ ሲሆኑ ትገዟቸው የነበራችሁት የት ናቸው። ይረዱዋችኋልን? ወይስ ለራሳቸው ይረዳሉን? በውስጧም እነርሱና ጠማሞች በፊቶቻቸው ተጥለው ይንከባለላሉ። የሰይጣንም ሰራዊቶች መላውም ይጣላሉ።

قَالُواْ وَهُمۡ فِيهَا يَخۡتَصِمُونَ ﴿٩٦﴾ تَٱللَّهِ إِن كُنَّا لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ﴿٩٧﴾ إِذۡ نُسَوِّيكُم بِرَبِّ
ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٩٨﴾ وَمَآ أَضَلَّنَآ إِلَّا ٱلۡمُجۡرِمُونَ ﴿٩٩﴾ فَمَا لَنَا مِن شَٰفِعِينَ ﴿١٠٠﴾ وَلَا صَدِيقٍ
حَمِيمٖ ﴿١٠١﴾ فَلَوۡ أَنَّ لَنَا كَرَّةٗ فَنَكُونَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿١٠٢﴾

**96-102.** እነርሱ በርሷ ውስጥ የሚከራከሩ ሆነው ይላሉ፡፡ በአላህ እንምላለን፤ እኛ በግልጽ መሳሳት ውስጥ ነብርን፡፡ ጣዖቶችን በዓለማት ጌታ ባስተካከልናችሁ ጊዜ፡፡ አመፀኞቹም እንጅ ሌላ አላሳሳተንም፡፡ ከአማላጆችም ለኛ ምንም የለንም፡፡ አዛኝ ወዳጅም የለንም፡፡ ለእኛም አንዲት ጊዜ መመለስ በኖረንና ከአማኞች በሆን እንመኛለን ይላሉ፡፡

إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ﴿١٠٣﴾ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١٠٤﴾

**103-104.** በዚህ ውስጥ አስደናቂ ግሣጼ አለበት፤ አብዛሀኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም፡፡ ጌታህም እርሱ በእርግጥ አሸናፊና አዛኝ ነው፡፡

كَذَّبَتۡ قَوۡمُ نُوحٍ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿١٠٥﴾ إِذۡ قَالَ لَهُمۡ أَخُوهُمۡ نُوحٌ أَلَا تَتَّقُونَ ﴿١٠٦﴾ إِنِّي لَكُمۡ رَسُولٌ
أَمِينٞ ﴿١٠٧﴾ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ﴿١٠٨﴾ وَمَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّ
ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٠٩﴾ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ﴿١١٠﴾

**105-110.** የኑህ ህዝቦች መልዕክተኞችን አስተባበሉ፡፡ ወንድማቸው ኑህ ለእነርሱ ባላቸው ጊዜ፡ አትጠነቀቁምን? እኔ ለእናንተ ታማኝ መልዕክተኛ ነኝ፡፡ አላህንም ፍሩ ታዘዙኝም፡፡ በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፤ ዋጋዬ ከዓለማት ጌታ እንጂ ከሌላ ላይ አይደለም፡፡ አላህንም ፍሩ፡፡ ታዘዙኝም፡፡

۞قَالُوٓاْ أَنُؤۡمِنُ لَكَ وَٱتَّبَعَكَ ٱلۡأَرۡذَلُونَ ﴿١١١﴾ قَالَ وَمَا عِلۡمِي بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿١١٢﴾ إِنۡ حِسَابُهُمۡ
إِلَّا عَلَىٰ رَبِّيۖ لَوۡ تَشۡعُرُونَ ﴿١١٣﴾ وَمَآ أَنَا۠ بِطَارِدِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿١١٤﴾ إِنۡ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٞ مُّبِينٞ ﴿١١٥﴾

**111-115.** እነርሱም ወራዶች የተከተሉህ ሆነህ ለአንተ እናምናለን? አሉት፡፡ እርሱም አላቸው፡- ይሰሩት በነበሩት ነገር ምን ዕውቀት አለኝ፡፡ ምርመራቸው በጌታዬ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ ብታውቁ ኖሮ ይህንን ትረዱት ነበር፡፡ እኔ አማኞችን አባራሪ አይደለሁም፡፡ እኔ እኮ ግልጽ አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም፡፡

قَالُواْ لَئِن لَّمۡ تَنتَهِ يَٰنُوحُ لَتَكُونَنَّ مِنَ ٱلۡمَرۡجُومِينَ ١١٦ قَالَ رَبِّ إِنَّ قَوۡمِي كَذَّبُونِ ١١٧
فَٱفۡتَحۡ بَيۡنِي وَبَيۡنَهُمۡ فَتۡحٗا وَنَجِّنِي وَمَن مَّعِيَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١١٨

**116-118.** ኑህ ሆይ! ከምትለው ባትከለከል በእርግጥ ከሚወገሩት ትሆናለህ አሉት። እርሱም አለ፡- ጌታየ ሆይ! ህዝቦቼ አስተባበሉኝ። በእኔና በእነርሱም መካከል ተገቢ ፍርድን ፍረድ። አድነኝም። ከእኔ ጋር ያሉትን ምዕመናንም አድን።

فَأَنجَيۡنَٰهُ وَمَن مَّعَهُۥ فِي ٱلۡفُلۡكِ ٱلۡمَشۡحُونِ ١١٩ ثُمَّ أَغۡرَقۡنَا بَعۡدُ ٱلۡبَاقِينَ ١٢٠ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ
لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ١٢١ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ١٢٢

**119-122.** እርሱንም ሆነ ከእርሱ ጋር ያለውን ሁሉ በተሞላው መርከብ ውስጥ አዳንን። ከዚያ በኋላ ቀሪዎችን አሰመጥን። በዚህ ውስጥ ታላቅ ግሣጼ አለበት አብዛሀኞቻቸውም አማኞች አልነበሩም። ጌታዬ እርሱ በእርግጥ አሸናፊና አዛኝ ነው።

كَذَّبَتۡ عَادٌ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ١٢٣ إِذۡ قَالَ لَهُمۡ أَخُوهُمۡ هُودٌ أَلَا تَتَّقُونَ ١٢٤ إِنِّي لَكُمۡ رَسُولٌ
أَمِينٞ ١٢٥ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ١٢٦ وَمَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَىٰ
رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٢٧ أَتَبۡنُونَ بِكُلِّ رِيعٍ ءَايَةٗ تَعۡبَثُونَ ١٢٨ وَتَتَّخِذُونَ مَصَانِعَ لَعَلَّكُمۡ
تَخۡلُدُونَ ١٢٩ وَإِذَا بَطَشۡتُم بَطَشۡتُمۡ جَبَّارِينَ ١٣٠ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ١٣١ وَٱتَّقُواْ ٱلَّذِيٓ
أَمَدَّكُم بِمَا تَعۡلَمُونَ ١٣٢ أَمَدَّكُم بِأَنۡعَٰمٖ وَبَنِينَ ١٣٣ وَجَنَّٰتٖ وَعُيُونٍ ١٣٤ إِنِّيٓ أَخَافُ
عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ١٣٥

**123-135.** ዓድ መልዕክተኞችን አስተባበለች፤ ወንድማቸው ሁድ ለእነርሱ ባላቸው ጊዜ አትጠነቀቁምን? እኔ ለእናንተ ታማኝ መልዕክተኛ ነኝ። አላህን ፍሩ ታዘዙኝም። በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አለመናችሁም። ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም። የምትጫወቱ ሆናችሁ በከፍተኛ ስፍራ ሁሉ ላይ ምልክት ትገነባላችሁን? የውሃ ማጠራቀሚያዎችንና ህንጻዎችንም ዘላለም መኖርን የምትከጅሉ ሆናችሁ ትሰራላችሁን? በቀጣችሁም ጊዜ ጨካኞች ሆናችሁ ትቀጣላችሁን? አላህንም ፍሩ። ታዘዙኝም። ያንንም የምታውቁት ፀጋ ያጣቀማችሁን በእንስሳዎችና በልጆች ያስደሰታችሁን በአትክልቶችና በምንጮችም ያጣቀማችሁን ጌታን ፍሩ። እኔ በእናንተ ላይ የታላቅን ቀን ቅጣት እፈራለሁና።

قَالُواْ سَوَآءٌ عَلَيۡنَآ أَوَعَظۡتَ أَمۡ لَمۡ تَكُن مِّنَ ٱلۡوَٰعِظِينَ ١٣٦
إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا خُلُقُ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٣٧ وَمَا نَحۡنُ بِمُعَذَّبِينَ ١٣٨

**136-138.** እነርሱም አሉ። ብትገስጽም ወይም ከገሳጮች ባትሆንም በእኛ ላይ እኩል ነው። (ያለንበትን አንለቅም)። ይህ የፊተኞቹ ሰዎች መንገድ እንጂ ሌላ አይደለም። እኛም የምንቀጣ አይደለንም አሉ።

فَكَذَّبُوهُ فَأَهۡلَكۡنَٰهُمۡۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ١٣٩
وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ١٤٠

**139-140.** አስተባበሉትም፤ አጠፋናቸውም፤ በዚህም ውስጥ እርግጠኛ ግሣጼም አለበት። አብዛኞቻቸውም ምዕምናን አልነበሩም። ጌታህም እርሱ በእርግጥ አሸናፊ፤ አዛኝ ነው።

كَذَّبَتۡ ثَمُودُ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ١٤١ إِذۡ قَالَ لَهُمۡ أَخُوهُمۡ صَٰلِحٌ أَلَا تَتَّقُونَ ١٤٢ إِنِّي لَكُمۡ رَسُولٌ
أَمِينٞ ١٤٣ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ١٤٤ وَمَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّ
ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٤٥ أَتُتۡرَكُونَ فِي مَا هَٰهُنَآ ءَامِنِينَ ١٤٦ فِي جَنَّٰتٖ وَعُيُونٖ ١٤٧ وَزُرُوعٖ وَنَخۡلٖ
طَلۡعُهَا هَضِيمٞ ١٤٨ وَتَنۡحِتُونَ مِنَ ٱلۡجِبَالِ بُيُوتٗا فَٰرِهِينَ ١٤٩ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ١٥٠ وَلَا
تُطِيعُوٓاْ أَمۡرَ ٱلۡمُسۡرِفِينَ ١٥١ ٱلَّذِينَ يُفۡسِدُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا يُصۡلِحُونَ ١٥٢

**141-152.** ሰሙድ መልዕክተኞችን አስተባበለች። ወንድማቸው ሷሊህ ለእነርሱ ባላቸው ጊዜ አትጠነቀቁምን? እኔ ለእናንተ ታማኝ መልዕክተኛ ነኝ? አላህን ፍሩ ታዘዙኝም። በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አልለምናችሁም። ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም። በዚያ እዚህ ባለው ፀጋ ውስጥ የረካችሁ ሆናችሁ ትተዋላችሁን? በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ በአዝመራዎችም ፍሬዋ የበሰለ በሆነች ዘንባባም ውስጥ ትተዋላችሁን? ብልሆች ሆናችሁ ከጋራዎች ቤቶችንም ትጠርባላችሁ። አላህንም ፍሩ፤ ታዘዙኝም። የወሰን አላፊዎችንም ትዕዛዝ አትከተሉ። የእነዚያን በምድር ላይ የሚያጠፉትንና የማያበጁትን።

قَالُوٓاْ إِنَّمَآ أَنتَ مِنَ ٱلۡمُسَحَّرِينَ ۝١٥٣ مَآ أَنتَ إِلَّا بَشَرٞ مِّثۡلُنَا
فَأۡتِ بِـَٔايَةٍ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ۝١٥٤

**153-154.** እነርሱም አሉ። አንተ በብዙ ከተደገመባቸው ሰዎች ብቻ ነህ። አንተ ብጤያችን ሰው እንጂ ሌላ አይደለህም። ከእውነተኞችም ከሆንክ ተዐምርን አምጣ።

قَالَ هَٰذِهِۦ نَاقَةٞ لَّهَا شِرۡبٞ وَلَكُمۡ شِرۡبُ يَوۡمٖ مَّعۡلُومٖ ۝١٥٥ وَلَا تَمَسُّوهَا بِسُوٓءٖ فَيَأۡخُذَكُمۡ
عَذَابُ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ۝١٥٦ فَعَقَرُوهَا فَأَصۡبَحُواْ نَٰدِمِينَ ۝١٥٧ فَأَخَذَهُمُ ٱلۡعَذَابُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ
لَأٓيَةٗۖ وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ۝١٥٨ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ۝١٥٩

**155-159.** (እርሱም) አለ ይህች ግመል ናት። ለእርሷ የመጠጥ ፋንታ አላት። ለእናንተም የታወቀ ቀን ፋንታ አላችሁ፤ በክፉም አትንኳት የታላቅ ቀን ቅጣት ይይዛችኋልና። ወጓትም ወዲያው ተፀፃቾች ሆነው አነጉ። ቅጣትም ያዛቸው በዚህም ውስጥ ግሣጼ አለበት አብዛኞቻቸውም ምዕመናን አልነበሩም። ጌታህም እርሱ በእርግጥ አሸናፊና አዛኝ ነው።

**ከባለቅኔዎች ምዕራፉ ከአንቀፅ (61-159) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በበኒ እስራኢሎች ላይ የነበረው የፊርዓውን ከፍተኛ ተፅዕኖ እና የባርነት አስተዳደር፤
2. ባህሩን በመከፈት አላህ ለሙሳ ያሳያቸውን ተዐምር፤
3. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤ በበኒ ኢስራኢሎች ላይ የነበረው የፊርዓውን ከፍተኛ ተፅዕኖ እና የባርነት አስተዳደር፤
4. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
5. ነብዩ ኢብራሂም ከሰዎቻቸው ጋር ያደረጉትን ውይይት በማውሳት ተውሒድን ማስተማር፤
6. ከአላህ ሌላ ያለን ያመለከ ሁሉ የቂያማ ቀን የአላህ ግልፅ ጠላቱ እንደሚሆን፤
7. ዳዕዋን በጥያቄና መልስ መልኩ ማስተማሩ ከዳዕዋ ስልቶች አንዱ ስለ መሆኑ
8. ጀነት የምትወረስና ወራሾቿም አላህን የሚፈሩ ሰዎች መሆናቸውን፤
9. ተውሒድን ይዘው ለሞቱ ወላጆች ምህረትን መለመን ተገቢ ስለመሆኑ፤
10. የቂያም ቀን በእምነት ላይ ተመስርቶ ያልተሰራ ስራ እርባና እንደሌለው፤
11. አላህን በመፍራት ላይ መገፋፋት እንዳለብን፤
12. ወደ ዝሙት፤ ወደ ወለድ እና ወደ መሳሰሉት መጥፎ ተግባራት ጥሪ የሚያደርጉት የዲያቢሎስ ሰራዊቶች ስለ መሆናቸው፤
13. አመፀኞች እራሳቸውንም አጥፍተው ሌላውንም እንደሚያጠፉ፤
14. በሽርክ ላይ ለሞተ ሰው ከአላህ ዘንድ ሽምግልና እንደማይጠቅመው፤
15. ቀድሞውኑ በአላህ ዘንድ ቀናው መንገድ እንደማይዙ የታወቁ ሰዎች ምክርም ሆነ ግሳፄ እንዲሁም ተዓምር ማሳየት እንደማይጠቅማቸው፤

16. አንድን ነብይ ያስተባበለ ሰው ሁሉንም ነብይ እንዳስተባበለ ስለ መሆኑ፤
17. የዝምድና ወንድማማችነት ከእምነት ወንድማማችነት ጋር እንደሚጋጭ፤
18. በዳዕዋ ስራ ላይ ክፍያን መጠየቅ አግባብ እንዳልሆነ፤
19. አላህን መፍራትና ነብዩን (ﷺ) መታዘዝ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
20. ለሀብታሞች ሲባል ድሆችን ከትምህርት ቦታ ማባረር ተገቢ እንዳልሆነ፤
21. አመፀኞች ጉዳያቸውን በማስረጃ ማቅረብት ሲያቅታቸው ወደ ጉልበት መጠቀም እንደሚያዘነብሉ፤
22. ተበዳይን እንዲረዳ አላህን መለመን ተገቢ ስለ መሆኑ፤
23. የዳዕዋን ዘዴዎችን መቀያየር ተገቢ ስለመሆኑ፤
24. ከአላህ ቅጣት አለመጠንቀቅና አላህን አለመታዘዝ ሊያስከትለው የሚችለውን መጥፎ ውድቀት
25. ሰዎች ያለፉ አባቶቻቸው መንገድ ስህተትም ቢሆን መከተላቸው የተለመደ ስለ መሆኑ፤
26. ነብይነትን፤ ተውሒድን፤ ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ
27. የነቢያት ጥሪ አንድ አይነት መሆኑን፤
28. ታማኝነት የሁሉም ነብያት ባህሪ መሆኑን፤
29. ሰዎች አላህን እንዲያስታውሱ የዋለላቸውን ፀጋ ማስታወስ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
30. በወንጀል ላይ ራሳቸውን ልቅ አድርገው ለሚኖሩ ሰዎች ከመታዘዝ ማስጠንቀቅ፤
31. ምድርን መበከል ማለት በውስጧ ወንጀል መስራት ማለት እንደሆነ፤
32. ድግምት ከድሮ ጀምሮ የሚሰራበት የሰው ልጆች ስራ እንደሆነ፤
33. የሰው ልጅ ወደ ኢስላም ሲጠራ ተአምር አሳዩኝ ማለቱ አዲስ እንዳልሆነ፤
34. ተዓምር ማሳየት የግድ ያሳምናል ማለት እንዳልሆነ፤
35. መፀፀት የተውበት አንዱ አካል ቢሆንም ቅጣትን በገሀድ ካዩ በኋላ መፀፀቱ ጠቀሜታ እንደሌለው እንማራለን።

كَذَّبَتۡ قَوۡمُ لُوطٍ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ١٦٠ إِذۡ قَالَ لَهُمۡ أَخُوهُمۡ لُوطٌ أَلَا تَتَّقُونَ ١٦١ إِنِّي لَكُمۡ رَسُولٌ
أَمِينٞ ١٦٢ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ١٦٣ وَمَآ أَسۡـَٔلُكُمۡ عَلَيۡهِ مِنۡ أَجۡرٍۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّ
ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٤ أَتَأۡتُونَ ٱلذُّكۡرَانَ مِنَ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٦٥ وَتَذَرُونَ مَا خَلَقَ لَكُمۡ رَبُّكُم مِّنۡ
أَزۡوَٰجِكُمۚ بَلۡ أَنتُمۡ قَوۡمٌ عَادُونَ ١٦٦

**160-166.** የሉጥ ህዝቦች መልዕክተኞችን አስተባበሉ። ወንድማቸው ሉጥ ለእነርሱ ባለ ጊዜ አትጠነቀቁምን? እኔ ለእናንተ ታማኝ መልዕክተኛ ነኝ። አላህንም ፍሩ ታዘዙኝም። በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አለምናችሁም። ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጅ በሌላ ላይ አይደለም። ከዓለማት ሰዎች መካከል የተለየ ወንዶችን ትገናኛላችሁን? ከሚስቶቻችሁም ጌታችሁ ለእናንተ የፈጠረላችሁን ትተዋላችሁን? በእውነት እናንተ ወሰን አላፊዎች ህዝቦች ናችሁ።

قَالُواْ لَئِن لَّمْ تَنتَهِ يَٰلُوطُ لَتَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُخْرَجِينَ ﴿١٦٧﴾

**167.** እነርሱም አሉ። ሉጥ ሆይ! ከዚህ ነገርህ ባትከለከል በእርግጥ በሀይል ከአገር ከሚወጡት ትሆናለህ።

قَالَ إِنِّي لِعَمَلِكُم مِّنَ ٱلْقَالِينَ ﴿١٦٨﴾ رَبِّ نَجِّنِي وَأَهْلِي مِمَّا يَعْمَلُونَ ﴿١٦٩﴾ فَنَجَّيْنَٰهُ وَأَهْلَهُۥٓ أَجْمَعِينَ ﴿١٧٠﴾ إِلَّا عَجُوزًا فِي ٱلْغَٰبِرِينَ ﴿١٧١﴾ ثُمَّ دَمَّرْنَا ٱلْـَٔاخَرِينَ ﴿١٧٢﴾ وَأَمْطَرْنَا عَلَيْهِم مَّطَرًاۖ فَسَآءَ مَطَرُ ٱلْمُنذَرِينَ ﴿١٧٣﴾ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةًۖ وَمَا كَانَ أَكْثَرُهُم مُّؤْمِنِينَ ﴿١٧٤﴾ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١٧٥﴾

**168-175.** እርሱም አለ እኔ ስራችሁን ከሚጠሉት ሰዎች አንዱ ነኝ። ጌታዬ ሆይ! እኔንም ሆነ ቤተሰቦቼን እነዚህ ህዝቦች ከሚሰሩት ስራ ቅጣት አድነን። እርሱንም ሆነ ቤተሰቦችንም በጠቅላላ አዳንናቸው። በቀሪዎች ውስጥ የሆነች አሮጊት በስተቀር (እርሷ ግን ጠፋች)። ከዚያም ሌሎችን አጠፋን። በእነርሱም ላይ (የድንጋይን) ዝናብን አዘነምንባቸው። የተስፈራሪዎችም ዝናም ምንኛ ከፋ። በዚህ ውስጥ አስደናቂ ተዐምር አለበት። አብዛኞቻቸውም ምዕምናን አልነበሩም። ጌታህም እርሱ አሸናፊና አዛኝ ነው።

كَذَّبَ أَصْحَٰبُ لْـَٔيْكَةِ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿١٧٦﴾ إِذْ قَالَ لَهُمْ شُعَيْبٌ أَلَا تَتَّقُونَ ﴿١٧٧﴾ إِنِّي لَكُمْ رَسُولٌ أَمِينٌ ﴿١٧٨﴾ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ﴿١٧٩﴾ وَمَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍۖ إِنْ أَجْرِيَ إِلَّا عَلَىٰ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٨٠﴾ ۞ أَوْفُواْ ٱلْكَيْلَ وَلَا تَكُونُواْ مِنَ ٱلْمُخْسِرِينَ ﴿١٨١﴾ وَزِنُواْ بِٱلْقِسْطَاسِ ٱلْمُسْتَقِيمِ ﴿١٨٢﴾ وَلَا تَبْخَسُواْ ٱلنَّاسَ أَشْيَآءَهُمْ وَلَا تَعْثَوْاْ فِي ٱلْأَرْضِ مُفْسِدِينَ ﴿١٨٣﴾ وَٱتَّقُواْ ٱلَّذِي خَلَقَكُمْ وَٱلْجِبِلَّةَ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿١٨٤﴾

**176-184.** የአይካ* ሰዎች መልዕክተኞችን አስተባበሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሹዐይብ ለእነርሱ አትጠነቀቁምን? እኔ ለእናንተ ታማኝ መልዕክተኛ ነኝ። አላህን ፍሩ፤ ታዘዙኝም። በእርሱም ላይ ምንም ዋጋ አልጠይቃችሁም፤ ዋጋዬ በዓለማት ጌታ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም። ስፍርን ሙሉ። ከአጎዳዮችም አትሁኑ ባላቸው ጊዜ የሆነውን አስታውስ። በትክክለኛ ሚዛንም መዝኑ። ሰዎችንም ነገሮቻቸውን አታጉድሉባቸው። በምድርም ላይ አጥፊዎች ሆናችሁ አታበላሹ። የፈጠራችሁን የቀድሞዎችንም ፍጡሮች የፈጠረውን ፍሩ።

* በአል-ሒጅር ምዕራፍ (78) ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ የተጻፈውን ማስታወሻን ተመልከት።

قَالُوٓاْ إِنَّمَآ أَنتَ مِنَ ٱلۡمُسَحَّرِينَ ١٨٥ وَمَآ أَنتَ إِلَّا بَشَرٞ مِّثۡلُنَا وَإِن نَّظُنُّكَ لَمِنَ
ٱلۡكَٰذِبِينَ ١٨٦ فَأَسۡقِطۡ عَلَيۡنَا كِسَفٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ١٨٧

**185-187.** አሉ፡- ሹዐይብ ሆይ! አንተ በብዛት ከተደገመባቸው ሰዎች አንዱ ነህ። አንተም ብጤያችን ሰው እንጂ ሌላ አይደለህም። እነሆ ከውሸታሞች ነህ ብለን እንጠረጥርሃለን፤ ከእውነተኞችም እንደሆንክ በእኛ ላይ ከሰማይ ቁራጭን ጣልብን።

قَالَ رَبِّيٓ أَعۡلَمُ بِمَا تَعۡمَلُونَ ١٨٨

**188.** ጌታዬ የምትሰሩትን ሁሉ ዐዋቂ ነው፤ አላቸው።

فَكَذَّبُوهُ فَأَخَذَهُمۡ عَذَابُ يَوۡمِ ٱلظُّلَّةِۚ إِنَّهُۥ كَانَ عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٍ ١٨٩ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗۖ
وَمَا كَانَ أَكۡثَرُهُم مُّؤۡمِنِينَ ١٩٠ وَإِنَّ رَبَّكَ لَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ١٩١

**189-191.** አስተባበሉትም የጥላይቱ ቀን ቅጣትም ያዛቸው፤ እርሱ የከባድ ቀን ቅጣት ነበርና። በዚህ ውስጥ አስደናቂ ተዐምር አለበት። አብዛኞቻቸውም ምዕመናን አልነበሩም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም እርሱ በእርግጥ አሸናፊና አዛኝ ነው።

وَإِنَّهُۥ لَتَنزِيلُ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٩٢ نَزَلَ بِهِ ٱلرُّوحُ ٱلۡأَمِينُ ١٩٣ عَلَىٰ قَلۡبِكَ لِتَكُونَ مِنَ
ٱلۡمُنذِرِينَ ١٩٤ بِلِسَانٍ عَرَبِيّٖ مُّبِينٖ ١٩٥

**192-195.** (ሙሐመድ ሆይ!) እርሱም ቁርኣን በእርግጥ ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው። እርሱን ታማኙ መንፈስ ጂብሪል አወረደው። ከአስፈራሪዎች ነብያት ትሆን ዘንድ በልብህ ላይ አወረደው፤ ግልጽ በሆነ ዐረብኛ ቋንቋ፤ (አወረደው)

وَإِنَّهُۥ لَفِي زُبُرِ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٩٦ أَوَلَمۡ يَكُن لَّهُمۡ ءَايَةً أَن يَعۡلَمَهُۥ عُلَمَٰٓؤُاْ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ١٩٧ وَلَوۡ
نَزَّلۡنَٰهُ عَلَىٰ بَعۡضِ ٱلۡأَعۡجَمِينَ ١٩٨ فَقَرَأَهُۥ عَلَيۡهِم مَّا كَانُواْ بِهِۦ مُؤۡمِنِينَ ١٩٩ كَذَٰلِكَ سَلَكۡنَٰهُ
فِي قُلُوبِ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ٢٠٠ لَا يُؤۡمِنُونَ بِهِۦ حَتَّىٰ يَرَوُاْ ٱلۡعَذَابَ ٱلۡأَلِيمَ ٢٠١ فَيَأۡتِيَهُم بَغۡتَةٗ وَهُمۡ
لَا يَشۡعُرُونَ ٢٠٢ فَيَقُولُواْ هَلۡ نَحۡنُ مُنظَرُونَ ٢٠٣ أَفَبِعَذَابِنَا يَسۡتَعۡجِلُونَ ٢٠٤ أَفَرَءَيۡتَ إِن
مَّتَّعۡنَٰهُمۡ سِنِينَ ٢٠٥ ثُمَّ جَآءَهُم مَّا كَانُواْ يُوعَدُونَ ٢٠٦ مَآ أَغۡنَىٰ عَنۡهُم مَّا كَانُواْ يُمَتَّعُونَ ٢٠٧

**196-207.** እርሱም (ቁርኣን) በቀድሞዎች መጽሐፍት ውስጥ የተወሳ ነው። የኢስራኤል ልጆች ሊቃውንት የሚያውቁት መሆኑ ለእነርሱ ለመካ ከሓዲያን ምልክት አይሆናቸውምን? ከአዕጀሞች ባንዱ ላይ ባወረድነውም ኖሮ በእነርሱ ላይ ባነበበውም በእርሱ አማኞች አይሆኑም ነበር። እንዲሁ ማስተባበልን በተንኮለኞች ልቦች ውስጥ አስገባነው። አሳማሚ ቅጣትን እስከሚያዩ ድረስ በእርሱ አያምኑም። እነርሱ የማያውቁ ሲሆኑ ቅጣቱ ድንገት እስከሚመጣባቸውም ድረስ አያምኑም። በመጣባቸው ጊዜ እኛ የምንቆይ ነን? እስሚሉም (አያምኑም)። በቅጣታችን ያቻኩላሉን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አየህን? ብዙ ዓመታትን ብናጣቅማቸው። ከዚያ ያ! ይስፈራሩበት የነበሩት ቢመጣባቸው። ይጣቀሙበት የነበሩት ሁሉ ከእነርሱ ምንም አያብቃቃቸውም።

وَمَآ أَهۡلَكۡنَا مِن قَرۡيَةٍ إِلَّا لَهَا مُنذِرُونَ ﴿٢٠٨﴾ ذِكۡرَىٰ وَمَا كُنَّا ظَٰلِمِينَ ﴿٢٠٩﴾ وَمَا تَنَزَّلَتۡ بِهِ
ٱلشَّيَٰطِينُ ﴿٢١٠﴾ وَمَا يَنۢبَغِي لَهُمۡ وَمَا يَسۡتَطِيعُونَ ﴿٢١١﴾ إِنَّهُمۡ عَنِ ٱلسَّمۡعِ لَمَعۡزُولُونَ ﴿٢١٢﴾
فَلَا تَدۡعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَتَكُونَ مِنَ ٱلۡمُعَذَّبِينَ ﴿٢١٣﴾

**208-213.** አንዲትንም ከተማ ለእርሷ አስፈራሪዎች ያሏት (እና ያስተባበለች) ሆና እንጂ አላጠፋንም። ይህች ግሣጼ ናት። በዳዮችም አልነበርንም። ሰይጣናትም እርሱን ቁርኣንን አላወረዱትም። ለእነርሱም አይገባቸውም አይችሉምም። እነርሱ የመላእክትን ንግግር ከመስማት የተከለከሉ ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ አትገዛ። ከሚቀጡት ትሆናለህና።

وَأَنذِرۡ عَشِيرَتَكَ ٱلۡأَقۡرَبِينَ ﴿٢١٤﴾ وَٱخۡفِضۡ جَنَاحَكَ لِمَنِ ٱتَّبَعَكَ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٢١٥﴾ فَإِنۡ
عَصَوۡكَ فَقُلۡ إِنِّي بَرِيٓءٞ مِّمَّا تَعۡمَلُونَ ﴿٢١٦﴾ وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱلۡعَزِيزِ ٱلرَّحِيمِ ﴿٢١٧﴾ ٱلَّذِي يَرَىٰكَ حِينَ
تَقُومُ ﴿٢١٨﴾ وَتَقَلُّبَكَ فِي ٱلسَّٰجِدِينَ ﴿٢١٩﴾ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ﴿٢٢٠﴾

**214-220.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቅርቦች ዘመዶችህንም* አስጠንቅቅ። (ሙሐመድ ሆይ)፣ ከምዕምናንም ለተከተሉህ ሰዎች ክንፍህን ዝቅ አድርግ ልዝብ ሁን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እንቢ ካሉህ እኔ ከምትሰሩት ወንጀል ሁሉ ንፁህ ነኝ በላቸው። (ሙሐመድ ሆይ!) አሸናፊና አዛኝ በሆነው ጌታህ ላይም ተጠጋ። በዚያ በሶላት በምትቆም ጊዜ በሚያይህ በሰጋጆችም ውስጥ መዘዋወርህንም በሚያየው ጌታህ ላይ ተጠጋ። እነሆ እርሱ ሰሚ፤ ዐዋቂ ነውና።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላፉት «የቅርብ ዘመዶችህንም አስጠንቅቅ» (አሽሹዐራእ፡ **214**) የሚለው ሲወርድ የአላህ መልዕክተኛ ሄዱና አስ. ሶፋ ተራራ ላይ ወጥተው «ያ ሰባሐህ!» ብለው ተጣሩ። ሰዎችም «ማነው እሱ?» ብለው ጠየቁ። ከዚያም ሁሉም በዙሪያቸው ተሰበሰቡ። እሳቸውም «ተመልከቱ! እኔ ከዚህ ተራራ በአንድ በኩል ጠላቶች እየመጡ ነው ብዬ ብነግራችሁ ታምኑኛላችሁን?» አሉ። ሰዎቹም «አንተ ሀሰት ተናግረህ ሰምተን አናውቅም» አሏቸው። እሳቸውም «ወደፊት ከሚመጣባችሁ ቅጣት አስጠንቃቂያችሁ ነኝ» አሉ። አቡ ለሀብም «ለዚህ ጉዳይ ነው የሰበሰብከን» አለና ሄደ። በዚህ ወቅት «አለለሀብ» የተሰኘው የቁርአን ምዕራፍ ወረደ»። «ያ ሰባሐህ» የሚለው ቃል የዐረብኛ ቃል ሲሆን የድረሱልኝን ወይም የእርዱኝን መልዕክት ለማስተላለፍ ዐረቦች የሚጠቀሙበት ቃል ነው።

هَلۡ أُنَبِّئُكُمۡ عَلَىٰ مَن تَنَزَّلُ ٱلشَّيَٰطِينُ ﴿٢٢١﴾ تَنَزَّلُ عَلَىٰ كُلِّ أَفَّاكٍ أَثِيمٖ ﴿٢٢٢﴾ يُلۡقُونَ ٱلسَّمۡعَ
وَأَكۡثَرُهُمۡ كَٰذِبُونَ ﴿٢٢٣﴾ وَٱلشُّعَرَآءُ يَتَّبِعُهُمُ ٱلۡغَاوُۥنَ ﴿٢٢٤﴾ أَلَمۡ تَرَ أَنَّهُمۡ فِي كُلِّ وَادٖ يَهِيمُونَ ﴿٢٢٥﴾
وَأَنَّهُمۡ يَقُولُونَ مَا لَا يَفۡعَلُونَ ﴿٢٢٦﴾ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَذَكَرُواْ ٱللَّهَ كَثِيرٗا
وَٱنتَصَرُواْ مِنۢ بَعۡدِ مَا ظُلِمُواْۗ وَسَيَعۡلَمُ ٱلَّذِينَ ظَلَمُوٓاْ أَيَّ مُنقَلَبٖ يَنقَلِبُونَ ﴿٢٢٧﴾

**221-227.** ሰይጣናት በማን ላይ እንደሚወርዱ ልንገራችሁን? በውሸታም ኃጢአተኛ ሁሉ ላይ ይወርዳሉ። የሰሙትን (ወደ ጠንቋዮች) ይጥላሉ። አብዛኞቻቸውም ውሸታሞች ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባለ ቅኔዎችንም ጠማማዎች ይከተሏቸዋል። እነርሱ (በንግግር) ሸለቆ ሁሉ የሚዋልሉ መሆናቸውን አታይምን? እነርሱም የማይሰሩትን ነገር የሚናገሩ መሆናቸውን አታይምን?። እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ስራዎችን የሰሩ አላህን በብዛት ያወሱ ከተበደሉም በኋላ (በቅኔ) የተከላከሉ ሲቀሩ፤ (እነርሱ አይወቀሱም) እነዚያም የበደሉ ከሞቱ በኋላ ያለን መመለስ እንደሚመለሱ በእርግጥ ያውቃሉ።

**ከባለቅኔዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (221-227) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በሀገር ብቻ መገናኘት ወንድም ለመባባል እንደሚያስችል፤
2. ነብይነትና ታማኝት የማይለያዩ ባህሪያት መሆናቸውን፤
3. ግለሰቦችም ሆኑ ህዝቦች ነፃ ለማውጣት ብቸኛው መንገድ አላህን መፍራትና ነብዩን ብቻ መታዘዝ መሆኑን፤
4. መጥፎ የሚሰራን ሰው ተግባሩን ማውገዝና ማጥላላት ግዴታ ስለ መሆኑ፤
5. በምድር ላይ ከተከሰቱት መጥፎ ወንጀሎች መካከል የግብረ ሰዶም ተግባር መሆኑን፤
6. አማኞች ከሀገር ለማባረር ማስፈራራት ቀድሞውኑ የነበረ የሰዎች ልምድ መሆኑን፤
7. መጥፎ ነገሮችን በየትኛውም መልኩ መጥላት ግዴታ ስለ መሆኑ፤
8. የተበዳዮችን ዱዓ አላህ እንደማይመልስ፤
9. ግፎች ሲበዙና ወንጀል ሲስፋፉ የአላህ ቁጣ እንደሚመጣ መጠባበቅ፤

10. ተዓምሮች የቱንም ያህል ቢገዝፉ ሊያሳምኑ እንደማይችሉ፤
11. ሰዎች አላህን እንዲፈሩ ማዘዝ የእያንዳንዱ የሀይማኖት አስተማሪ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
12. ሀይማኖት የሚያስተምር ሰው ደመወዝ ከፈሉኝ ማለት እንደሌለበት፤
13. ስፍርንና ሚዛንን ማንሸራተት ክልክል መሆኑን፤
14. ሰዎችን መብታቸውን መግፈፍ በየትኛውም መልኩ ማጓደል የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
15. የሁሉም ነብያት ጥሪ አንድ መሆኑን፤
16. ሰዎች የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ሰው መሆን አይገባውም ማለታቸው የተለመደ አባባል መሆኑን፤
17. ተዓምር አምጡልኝ በማለት የሚያምኑት ጥቂቶች ቢሆኑም የሁሉም አባባል እንደነበር፤
18. ተውሒድን፤ ሙቶ መነሳትንና ነብይነትን ማረጋገጥ፤
19. የወህይን ሀቅነትና የነብዩን ነብይነት ማፅደቅ፤
20. ለነብዩ (ﷺ) ቁርኣንን ያመጣ የነበረው መልአኩ ጅብሪል መሆኑን ማረጋገጥ፤
21. የነብዩን (ﷺ) የነብይነትና ተልዕኮ ማስፈራራት ስለመሆኑ፤
22. ቁርኣን በመፅሀፍት ሰዎች ራሳቸው በሰጡት ምስክርነት በቀደምት መፅሐፍቶች የተወሳ መሆኑን፤
23. ወንጀል ሲበዛና ሲደራረብ ከተውበትና ከእምነት እንደሚከለክል፤
24. አመፀኞች ቅጣትን በአይናቸው ሲያዩ ተውበትን የሚመኙ ቢሆንም ተቀባይነት እንደሌለው፤
25. የአላህ ቅጣት አሁኑኑ ይምጣልን እያሉ ማጣደፍ ሞኝነትና የአዕምሮን መካንነት የሚያሳይ ነው።
26. የእድሜ መርዘም የሲሳይ መብዛት የአላህ ቅጣት በመጣ ጊዜ ምንም እንደማይፈይድ፤
27. አላህ የትኛውንም ህዝብ ሳያስተምርና ሳያስጠነቅቅ አጥፍቶ (ተቆጥቶ) እንደማያውቅ፤
28. ቁርኣን የመካ ከሓዲያን የጠንቋዮች ንግግር፤ የሰይጣኖች ተልዕኮ ነው እንደሚሉት አለመሆኑ፤
29. ከአላህ ሌላ ያለን ፍጡር ማምለክ ክልክል ስለመሆኑ ማረጋገጥ፤
30. ከአላህ ሌላ ማንንም እያመለከ የሞተ ሰው ያለምንም ጥርጥር ለእሳት እንደሚዳርግ፤
31. በሁሉም ነገር ላይ በዘመዶች መጀመር ተገቢ ስለሆነ፤
32. ምእመናን ጎንን ለስላሳ አድርጎ ተናንሶ በተለይም ለአዲስ ሰራተኞች ልዩ እንክብካቤ ማድረግ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
33. ከማጋራትና ከአጋሪዎች ራስን ማግለል አማራጭ የሌለው መሆኑን፤
34. በአላህ ላይ መመካት ግዴታ ስለመሆኑ፤
35. የሌሊት ሶላትና የጀመዓ ሶላት ለሰው ልጆች የሚሰጡትን ጥቅም ማስታወስ፤
36. ነብዩን (ﷺ) ጠንቋይና ዘፋኝ ናቸው የሚለውን አባባል ማውገዝ፤
37. ሰይጣን በወንጀል ከቆሸሹ መንፈሶች ጋር ትስስር እንዳለው፤
38. ዘፋኞችን በየጊዜው የሚከተሏቸው ጋጠወጦች እንደሆኑ፤
39. ግጥም መግጠም ለማስተማርና ወይም ከኢስላም ለመከላከል ከሆነ እንደሚፈቀድ፤
40. ግፈኝነት መጨረሻው አስቀያሚ ስለሆነ መጠንቀቅ እንደሚገባ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የባለቅኔዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (27)
# የጉንዷኗ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አንነምል)

سُورَةُ النَّمۡلِ

**የወረደው በመካ ነው። የምራፉ አናቅፅ ብዛት (93) ናቸው።**

**የሱረቱ አን-ነምል መግቢያ**

የቁርኣንን ተዓምርነት በማመልከት ይጀምራል። የነብዩ ሙሳን ተዓምርና አንዳንድ የታሪክ ዘገባ፤ የዳውድና የሱለይማንን ታሪክ እና የተሰጣቸውን ተዓምር፤ ሁድሁድ የተባለውን ወፍ ታሪክ የብልቂስንና የተከታዩን ታሪክ በሰፊው ይተርካል። የነብዩ ሳሊህንና የነብዩ ሉጥን ታሪክም ቀንጩብ አድርጎ ያወሳል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

طسٓۚ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡقُرۡءَانِ وَكِتَابٖ مُّبِينٍ ١ هُدٗى وَبُشۡرَىٰ لِلۡمُؤۡمِنِينَ ٢ ٱلَّذِينَ يُقِيمُونَ
ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَهُم بِٱلۡأٓخِرَةِ هُمۡ يُوقِنُونَ ٣

**1-3.** ጣ፤ ሲን፤* ይህ ከቁርአኑና ከገላጩ መጽሐፍ አንቀፆች (የተወሰነ) ነው። ለምዕምናን መሪና ብስራት ነው። ለእነዚያ ሶላትን ለሚሰግዱት፤ ዘካንም ለሚሰጡ፤ እነርሱም በመጨረሻይቱ ሕይወት እነርሱ የሚያረጋግጡ ለሆኑት።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِ زَيَّنَّا لَهُمۡ أَعۡمَٰلَهُمۡ فَهُمۡ يَعۡمَهُونَ ٤ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَهُمۡ سُوٓءُ
ٱلۡعَذَابِ وَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ هُمُ ٱلۡأَخۡسَرُونَ ٥ وَإِنَّكَ لَتُلَقَّى ٱلۡقُرۡءَانَ مِن لَّدُنۡ حَكِيمٍ عَلِيمٍ ٦

**4-6.** እነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት ለእነርሱ ክፉ ሥራዎቻቸውን ሸለምንላቸው። ስለዚህ እነርሱ ይዋልላሉ። እነርሱ እነዚያ ክፉ ቅጣት ለእነርሱ ያላባቸው ናቸው። እነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም እነርሱ በጣም ከከሳሪዎቹ ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተም ቁርኣንን ጥበበኛና ዐዋቂ ከሆነው ጌታህ ዘንድ በእርግጥ ትስሰጣለህ።

إِذۡ قَالَ مُوسَىٰ لِأَهۡلِهِۦٓ إِنِّيٓ ءَانَسۡتُ نَارٗا سَـَٔاتِيكُم مِّنۡهَا بِخَبَرٍ
أَوۡ ءَاتِيكُم بِشِهَابٖ قَبَسٖ لَّعَلَّكُمۡ تَصۡطَلُونَ ٧

**7.** ሙሳ ለቤተሰቦቹ እኔ እሳትን አየሁ ከእርሷ ወሬን አመጣላችኋለሁ ወይም ትሞቁ ዘንድ የተለኮሰ ችቦን አመጣላችኋለሁ ባለ ጊዜ (የሆነውን አውሳላቸው)።

فَلَمَّا جَآءَهَا نُودِيَ أَنۢ بُورِكَ مَن فِي ٱلنَّارِ وَمَنۡ حَوۡلَهَا وَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٨
يَٰمُوسَىٰٓ إِنَّهُۥٓ أَنَا ٱللَّهُ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٩ وَأَلۡقِ عَصَاكَۚ فَلَمَّا رَءَاهَا تَهۡتَزُّ كَأَنَّهَا جَآنّٞ وَلَّىٰ
مُدۡبِرٗا وَلَمۡ يُعَقِّبۡۚ يَٰمُوسَىٰ لَا تَخَفۡ إِنِّي لَا يَخَافُ لَدَيَّ ٱلۡمُرۡسَلُونَ ١٠ إِلَّا مَن ظَلَمَ ثُمَّ

بَدَّلَ حُسۡنَۢا بَعۡدَ سُوٓءٖ فَإِنِّي غَفُورٞ رَّحِيمٞ ١١ وَأَدۡخِلۡ يَدَكَ فِي جَيۡبِكَ تَخۡرُجۡ بَيۡضَآءَ مِنۡ
غَيۡرِ سُوٓءٖۖ فِي تِسۡعِ ءَايَٰتٍ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ وَقَوۡمِهِۦٓۚ إِنَّهُمۡ كَانُواْ قَوۡمٗا فَٰسِقِينَ ١٢ فَلَمَّا جَآءَتۡهُمۡ
ءَايَٰتُنَا مُبۡصِرَةٗ قَالُواْ هَٰذَا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ١٣ وَجَحَدُواْ بِهَا وَٱسۡتَيۡقَنَتۡهَآ أَنفُسُهُمۡ ظُلۡمٗا وَعُلُوّٗاۚ
فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ١٤

**8-14.** በመጣትም ጊዜ እንዲህ በማለት ተጠራ፦ በእሳቲቱ ያለው ሰውና በዙሪያዋ ያሉም ሰዎች ሁሉ ተባረኩ። የዓለማትም ጌታ አላህ ጥራት ይገባው። ሙሳ ሆይ! እነሆ እኔ አሸናፊና ጥበበኛ አላህ ነኝ። በትርህንም ጣል (ተባለና ጣለም)። እርሷ እንደ ትንሽ እባብ በፍጥነት ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ ፊቱን አዙሮ ሸሸ። አልተመለሰምም። ሙሳ ሆይ! አትፍራ። እኔ መልዕክተኞች እኔ ዘንድ ፈፅሞ አይፈሩምና። ግን የበደለ ሰው ከዚያ ከመጥፎ ሥራው በኋላ መልካምን የለወጠ እኔ መሓሪ፤ አዛኝ ነኝ። እጅህንም በአንገትህ ውስጥ አስገባ ያለ ነውር ያለ ለምጽ ነጭ ሆና ትወጣለችና በዘጠኝ ታዐምራት ወደ ፈርኦንና ወደ ሕዝቦቹ ሂድ እነርሱ አመፀኞች ህዝቦች ናቸውና። ታምራቶቻችንም ግልጽ ሆና በመጣቻቸው ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው አሉ። ነፍሶቻቸውም ያረጋገጧት ሲሆኑ ለበደልና ለኩራት በእርሷ ካዱ። የአመፀኞችም ፍጻሜ እንዴት እንደነበረ ተመልከት።

**ከጉንዳኗ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-14) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. *እምነትን በውስጥ ማረጋገጥና በተግባር መፈፀም ሲሆን በቁርአን ለመጠቀም ዋናው ቁልፍ እንደሆነ፤*
2. *መጥፎነትና ደግነት ከሸሪዓ አንፃር እንጂ በሌላ መስፈርት እንዳልሆነ፤*
3. *አላህ ሁሉን ነገር ሲፈፅም በእውቀትና በጥበብ ላይ ተመስርቶ እንደሆነ፤*
4. *የሲና ተራራ የተከበረ ቦታና ሙሳ ለነብይነት የተመረጡበት መሆኑን፤*
5. *ነብያት ከአላህ ቅጣት ነፃ መሆናቸውን፤*
6. *አጥፊዎች ሲፀፀቱ ወንጀለኞች ንስሃ ሲገቡ ይቅር ማለቱ ከአላህ ሩህሩህነት መገለጫዎች መሆናቸውን እንማራለን።*

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ وَسُلَيۡمَٰنَ عِلۡمٗاۖ وَقَالَا ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِي فَضَّلَنَا عَلَىٰ كَثِيرٖ مِّنۡ عِبَادِهِ
ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١٥ وَوَرِثَ سُلَيۡمَٰنُ دَاوُۥدَۖ وَقَالَ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ عُلِّمۡنَا مَنطِقَ ٱلطَّيۡرِ وَأُوتِينَا
مِن كُلِّ شَيۡءٍۖ إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ ٱلۡفَضۡلُ ٱلۡمُبِينُ ١٦ وَحُشِرَ لِسُلَيۡمَٰنَ جُنُودُهُۥ مِنَ ٱلۡجِنِّ وَٱلۡإِنسِ
وَٱلطَّيۡرِ فَهُمۡ يُوزَعُونَ ١٧ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَتَوۡاْ عَلَىٰ وَادِ ٱلنَّمۡلِ قَالَتۡ نَمۡلَةٞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّمۡلُ ٱدۡخُلُواْ

مَسَٰكِنَكُمۡ لَا يَحۡطِمَنَّكُمۡ سُلَيۡمَٰنُ وَجُنُودُهُۥ وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ١٨ فَتَبَسَّمَ ضَاحِكٗا مِّن
قَوۡلِهَا وَقَالَ رَبِّ أَوۡزِعۡنِيٓ أَنۡ أَشۡكُرَ نِعۡمَتَكَ ٱلَّتِيٓ أَنۡعَمۡتَ عَلَيَّ وَعَلَىٰ وَٰلِدَيَّ وَأَنۡ أَعۡمَلَ
صَٰلِحٗا تَرۡضَىٰهُ وَأَدۡخِلۡنِي بِرَحۡمَتِكَ فِي عِبَادِكَ ٱلصَّٰلِحِينَ ١٩

**15-19.** ለዳውድና ለሱለይማን እውቀትን በእርግጥ ሰጠናቸው። ምስጋና ሁሉ ለአላህ ለዚያ ከምዕመናን ባሮቹ በብዙዎቹ ላይ ላበለጠን ይገባው አሉም። ሱለይማንም ዳውድን ወረሰ። አለምም ሰዎች ሆይ የበራሪን ንግግር የወፍን ቋንቋ ተስተማርን ከነገሩም ሁሉ ተሰጠን ይህ እርሱ በእርግጥ ግልጽ የሆነ ችሮታ ነው። ለሱለይማንም ከአጋንንት ከሰውም ከበራሪም የሆኑት ሰራዊቶቹ ተሰበሰቡ። እነርሱም ይከመከማሉ። በጉንዳንም ሸለቆ በመጡ ጊዜ አንዲት ጉንዳን፡- እናንተ ጉንዳኖች ሆይ፣ ወደ መኖሪያዎቻችሁ ግቡ። ሱለይማንና ሰራዊቱ እነርሱ የማያውቁ ሲሆኑ እንዳይሰባብሯችሁ አለች። ከንግግርዋም እየሳቀ ጥርሱን ፈገግ አደረገ። ጌታዬ ሆይ፣ ያቺን በእኔና በወላጆቼ ላይ የለገስካትን ፀጋህን እንዳመሰግን የምትወደውንም በጎ ሥራ እንድሠራ ምራኝ በችሮታህም በመልካሞቹ ባሮችህ ውስጥ አስገባኝ አለ።

وَتَفَقَّدَ ٱلطَّيۡرَ فَقَالَ مَالِيَ لَآ أَرَى ٱلۡهُدۡهُدَ أَمۡ كَانَ مِنَ ٱلۡغَآئِبِينَ ٢٠ لَأُعَذِّبَنَّهُۥ عَذَابٗا
شَدِيدًا أَوۡ لَأَاْذۡبَحَنَّهُۥٓ أَوۡ لَيَأۡتِيَنِّي بِسُلۡطَٰنٖ مُّبِينٖ ٢١ فَمَكَثَ غَيۡرَ بَعِيدٖ فَقَالَ أَحَطتُ بِمَا
لَمۡ تُحِطۡ بِهِۦ وَجِئۡتُكَ مِن سَبَإِۭ بِنَبَإٖ يَقِينٍ ٢٢ إِنِّي وَجَدتُّ ٱمۡرَأَةٗ تَمۡلِكُهُمۡ وَأُوتِيَتۡ مِن كُلِّ
شَيۡءٖ وَلَهَا عَرۡشٌ عَظِيمٞ ٢٣ وَجَدتُّهَا وَقَوۡمَهَا يَسۡجُدُونَ لِلشَّمۡسِ مِن دُونِ ٱللَّهِ وَزَيَّنَ لَهُمُ
ٱلشَّيۡطَٰنُ أَعۡمَٰلَهُمۡ فَصَدَّهُمۡ عَنِ ٱلسَّبِيلِ فَهُمۡ لَا يَهۡتَدُونَ ٢٤ أَلَّاۤ يَسۡجُدُواْۤ لِلَّهِ ٱلَّذِي يُخۡرِجُ
ٱلۡخَبۡءَ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَيَعۡلَمُ مَا تُخۡفُونَ وَمَا تُعۡلِنُونَ ٢٥ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ رَبُّ
ٱلۡعَرۡشِ ٱلۡعَظِيمِ۩ ٢٦

**20-26.** በራሪዎቹንም ተመለከተ። ከዚያ ሁድሁድን ለምን አላየሁትም! በእውነቱ ከራቁት ነበርን?። ብርቱን ቅጣት በእርግጥ እቀጣዋለሁ። ወይም በእርግጥ አርደዋለሁ። ወይም ግልጽ የሆነ አስረጅን ያቀርብልኛል አለ። (ሁድሁድ የተባለው ወፍ) እሩቅ ያልሆነንም ጊዜ ቆየ። ከዚያ አለ ያላወቅከውን ነገር አወቅኩ ከሰበእም እርግጠኛን ወሬ አመጣሁልህ። እኔ የምትገዛቸው የሆነችን ሴት ከነገሩም ሁሉ የተሰጠችን አገኘሁ። ለእርሷም ታላቅ ዙፋን አላት

አለ። እርስዋንም ሕዝቦችዋንም ከአላህ ሌላ ለፀሐይ ሲሰግዱ አገኘኋቸው ሰይጣንም ለእነርሱ ሥራዎቻቸውን ሸልሞላቸዋል ከእውነተኛውም መንገድ አግዷቸዋል። ስለዚህ እነርሱ ወደ እውነት አይመሩም። ለዚያ በሰማያትና በምድር ዉስጥ የተደበቀውን ለሚያወጣው የምትሸሽጉትንና የምትገልፁትንም ሁሉ ለሚያውቀው አላህ እንዳይሰግዱ ሰይጣን አግዷቸዋል። አላህ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። የታላቁ ዐርሽ (ዙፋን) ጌታ ነው።

۞قَالَ سَنَنظُرُ أَصَدَقْتَ أَمْ كُنتَ مِنَ ٱلْكَـٰذِبِينَ ﴿٢٧﴾ ٱذْهَب بِّكِتَـٰبِى هَـٰذَا فَأَلْقِهْ إِلَيْهِمْ ثُمَّ تَوَلَّ عَنْهُمْ فَٱنظُرْ مَاذَا يَرْجِعُونَ ﴿٢٨﴾ قَالَتْ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلْمَلَؤُا۟ إِنِّىٓ أُلْقِىَ إِلَىَّ كِتَـٰبٌ كَرِيمٌ ﴿٢٩﴾ إِنَّهُۥ مِن سُلَيْمَـٰنَ وَإِنَّهُۥ بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَـٰنِ ٱلرَّحِيمِ ﴿٣٠﴾ أَلَّا تَعْلُوا۟ عَلَىَّ وَأْتُونِى مُسْلِمِينَ ﴿٣١﴾

**27-31.** ሱለይማንም አለ፡- እውነት እንደ ተናገርክ ወይም ከውሸታሞቹ እንደሆንክ ወደ ፊት እናያለን። ይህንን ደብዳቤዬን ይዘህ ሂድ ወደ እነርሱም ጣለው ከዚያ ከእነርሱ ዘወር በል ምን እንደሚመልሱም ተመልከት። እርሷም በደረሳት ጊዜ አለች፡- እናንተ መማክርቶች ሆይ፣ እኔ ክብር ያለው ጽሑፍ ወደ እኔ ተጣለ። እርሱ ከእሱለይማን ነው። እርሱም በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው። በእኔ ላይ አትኩሩ። ታዛዦችም ሆናችሁ ወደ እኔ ኑ። የሚል ነው።

قَالَتْ يَـٰٓأَيُّهَا ٱلْمَلَؤُا۟ أَفْتُونِى فِىٓ أَمْرِى مَا كُنتُ قَاطِعَةً أَمْرًا حَتَّىٰ تَشْهَدُونِ ﴿٣٢﴾ قَالُوا۟ نَحْنُ أُو۟لُوا۟ قُوَّةٍ وَأُو۟لُوا۟ بَأْسٍ شَدِيدٍ وَٱلْأَمْرُ إِلَيْكِ فَٱنظُرِى مَاذَا تَأْمُرِينَ ﴿٣٣﴾ قَالَتْ إِنَّ ٱلْمُلُوكَ إِذَا دَخَلُوا۟ قَرْيَةً أَفْسَدُوهَا وَجَعَلُوٓا۟ أَعِزَّةَ أَهْلِهَآ أَذِلَّةً ۖ وَكَذَٰلِكَ يَفْعَلُونَ ﴿٣٤﴾ وَإِنِّى مُرْسِلَةٌ إِلَيْهِم بِهَدِيَّةٍ فَنَاظِرَةٌۢ بِمَ يَرْجِعُ ٱلْمُرْسَلُونَ ﴿٣٥﴾

**32-35.** እናንተ መማክርቶች ሆይ፣ በነገሬ የሚበጀውን ንገሩኝ እስከምትገኙልኝ ድረስ አንድንም ነገር ቆራጭ አይደለሁምና አለች። እኛ የሀይል ባለቤቶች የብርቱ ጦርም ባለቤቶች ነን። ግን ትዕዛዙ ወደ አንቺ ብቻ ነው። ምን እንደምታዝዢንም አስተውይ አሏት። እርሷም አለች፡- ንጉሶች ከተማን በሃይል በገቡባት ጊዜ ያበላሿታል የተከበሩ ሰዎችዋንም ወራዶች ያደርጋሉ። እንደዚሁም እነዚህ ይሠራሉ። እኔ ወደ እነርሱ ገፀበረከትን የምልክና መልዕክተኞቹ በምን እንደሚመለሱ የምጠባበቅ ነኝ።

**ከጉንዳኗ ምዕራፍ ከአንቀፅ (15-35) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ስለ እውቀት ትልቅነትና እውቀትን ለሰው ልጆች ጥቅምና ለእምነት መጨመሪያ ማዳበሪያ ማዋል ተገቢ ስለመሆኑ፤
2. በራሪ እንስሳዎች የራሳቸው የሆነ መግባቢያ ቋንቋ እንዳላቸው፤
3. ሀላፊ የሆነ ሰው በሀላፊነት ተጠያቂ እንደሚሆን ማሰብ እንዳለበት፤
4. ከሌሎች ተሞክሮና ልምድ መማር ተገቢ ስለመሆኑ፤ ስራም ሆነ ሰራተኛ የቱንም ያህል ቢያንስ ሊናቅ እንደማይገባ፤
5. አስተምህሮት በጥበብና በመልካም ምክር መሆን እንዳለበት፤
6. ወለድ ለግለሰብ ሆነ ለማህበረሰብ የሚያበላሽ መሆኑን እና ጉቦ የተከለከለ መሆኑን፤
7. የንግስት ቢልቂስ ግንዛቤ ምን ያህል የመጠቀ እንደነበረ፤
8. አላህ ለነብዩ ሱለይማን የሰጣቸው ትልቅ ትሩፋት እንደነበር እንማራለን።

فَلَمَّا جَآءَ سُلَيۡمَٰنَ قَالَ أَتُمِدُّونَنِ بِمَالٖ فَمَآ ءَاتَىٰنِۦَ ٱللَّهُ خَيۡرٞ مِّمَّآ ءَاتَىٰكُمۚ بَلۡ أَنتُم
بِهَدِيَّتِكُمۡ تَفۡرَحُونَ ٣٦ ٱرۡجِعۡ إِلَيۡهِمۡ فَلَنَأۡتِيَنَّهُم بِجُنُودٖ لَّا قِبَلَ لَهُم بِهَا وَلَنُخۡرِجَنَّهُم مِّنۡهَآ
أَذِلَّةٗ وَهُمۡ صَٰغِرُونَ ٣٧

**36-37.** መልዕክተኛው ሱለይማንንም በመጣው ጊዜ አለ፡- በገንዘብ ትረዱኛላችሁን? አላህም የሰጠኝ ከሰጣችሁ የበለጠ ነው። ይልቁንም እናንተ በገፀበረከታችሁ ትደሰታላችሁ። ወደ እነርሱ ተመለስ። ለእነርሱም በእርሷ ችሎታ በሌላቸው ሰራዊት እንመጣባቸዋለን። ከእርሷም እነርሱ የተዋረዱ ሆነው በእርግጥ እናወጣቸዋለን አለ።

قَالَ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمَلَؤُاْ أَيُّكُمۡ يَأۡتِينِي بِعَرۡشِهَا قَبۡلَ أَن يَأۡتُونِي مُسۡلِمِينَ ٣٨ قَالَ عِفۡرِيتٞ مِّنَ
ٱلۡجِنِّ أَنَا۠ ءَاتِيكَ بِهِۦ قَبۡلَ أَن تَقُومَ مِن مَّقَامِكَۖ وَإِنِّي عَلَيۡهِ لَقَوِيٌّ أَمِينٞ ٣٩ قَالَ ٱلَّذِي
عِندَهُۥ عِلۡمٞ مِّنَ ٱلۡكِتَٰبِ أَنَا۠ ءَاتِيكَ بِهِۦ قَبۡلَ أَن يَرۡتَدَّ إِلَيۡكَ طَرۡفُكَۚ فَلَمَّا رَءَاهُ مُسۡتَقِرًّا
عِندَهُۥ قَالَ هَٰذَا مِن فَضۡلِ رَبِّي لِيَبۡلُوَنِيٓ ءَأَشۡكُرُ أَمۡ أَكۡفُرُۖ وَمَن شَكَرَ فَإِنَّمَا يَشۡكُرُ
لِنَفۡسِهِۦۖ وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ رَبِّي غَنِيّٞ كَرِيمٞ ٤٠

**38-40.** እናንተ መኳንንቶች ሆይ፣ ሙስሊሞች ሆነው ወደ እኔ ሳይመጡ በፊት ዙፋንዋን የሚያመጣልኝ ማንኛችሁ ነው? አለ። ከአጋንንት ሀይለኛው ከችሎትህ ከመነሳትህ በፊት እኔ እርሱን አመጣልሃለሁ። እኔም በእርሱ ላይ ብርቱ ታማኝ ነኝ አለ። ያ፣ እርሱ ዘንድ ከመጽሐፍ ጥልቅ ዕውቀት* ያለው ሰው የተገለፀው ዓይንህ ወደ አንተ ከመመለሱ በፊት እኔ እርሱን አመጣልሃለሁ

አለ። እንደዚሁም አደረገ። እርሱ ዘንድ ረግቶ ባየውም ጊዜ ይህ ከጌታዬ ችሮታዎች አንዱ ነው አለ። የማመሰግን ወይም የምክድ መሆኔን ሊሞክረኝ ቸረኝ። አላህን ያመሰገነ ሰው የሚያመሰግነው ለራሱ ነው። አላህን የካደም ሰው ጌታዬ ከእርሱ ተብቃቂ፣ ቸር ነው አለ።

✷ ይህ እዚህ ላይ እውቀት ያለው የተባለው አካል ማንነትን በተመለከተ በምሁራን ብዙ የተባለ ቢሆንም አብዛሃኛወች ሙፈሲሮች ያሉት ግን ከሱለይማን ጋር ካሉት ሰወች አንዱ ነው የሚለው ነው።

قَالَ نَكِّرُواْ لَهَا عَرْشَهَا نَنظُرْ أَتَهْتَدِىٓ أَمْ تَكُونُ مِنَ ٱلَّذِينَ لَا يَهْتَدُونَ ﴿٤١﴾ فَلَمَّا جَآءَتْ
قِيلَ أَهَٰكَذَا عَرْشُكِۖ قَالَتْ كَأَنَّهُۥ هُوَۚ وَأُوتِينَا ٱلْعِلْمَ مِن قَبْلِهَا وَكُنَّا مُسْلِمِينَ ﴿٤٢﴾
وَصَدَّهَا مَا كَانَت تَّعْبُدُ مِن دُونِ ٱللَّهِۖ إِنَّهَا كَانَتْ مِن قَوْمٍ كَٰفِرِينَ ﴿٤٣﴾ قِيلَ لَهَا ٱدْخُلِى
ٱلصَّرْحَۖ فَلَمَّا رَأَتْهُ حَسِبَتْهُ لُجَّةً وَكَشَفَتْ عَن سَاقَيْهَاۚ قَالَ إِنَّهُۥ صَرْحٌ مُّمَرَّدٌ مِّن قَوَارِيرَۗ
قَالَتْ رَبِّ إِنِّى ظَلَمْتُ نَفْسِى وَأَسْلَمْتُ مَعَ سُلَيْمَٰنَ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٤٤﴾

**41-44.** ዙፋንዋን ለእርሷ አሳስቱ ታውቀው እንደሆነ ወይም ከእነዚያ ከማያውቁት ትሆን እንደሆነ እናያለን አላቸው። በመጣችም ጊዜ:- ዙፋንሽ እንደዚህ ነውን? ተባለች እርሱ ልክ እርሱ ነው መሰለኝ አለች ሱለይማን ከእርሷ በፊትም እውቀትን ተሰጠን ሙስሊሞችም ነበርን አለ። ከአላህ ሌላ ትገዛው የነበረችውንም ከለከላት። እርሷ ከከሓዲዎች ሕዝቦች ነበረችና። ሕንጻውን ግቢ ተባለች። ባየችውም ጊዜ ባህር ነው ብላ ጠረጠረችው ከባቶቿም ገለጠች እርሱ ከመስተዋት የተለሰለሰ ህንጻ ነው አሏት። ጌታዬ ሆይ፣ እኔ ነፍሴን በደልኩ ከሱለይማንም ጋር ሆኜ ለዓለማት ጌታ ለአላህ ታዘዝኩ አለች።

**ከጉንዳኗ ምዕራፍ ከአንቀፅ (36-44) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. በአላህ ማመንና ከእሱ ጋር ያለን ግንኙነት ማጠናከር የተለየ ሥጦታና አቅም እንደሚሰጥ፣
2. ትክክለኛ እምነት ወይም አማኝነት ማለት ሁለንተናን ለአላህ ጠቅልሎ መስጠትና ለአላህ ሁለንተናቸውን ጠቅልለው ከሰጡ ደጋግ ሰዎች፣ ከነብያትና የነሱን መንገድ ከተከተሉት ጋር መተባበር ሲሆን ይህ ማለት ግን እነሱን ከአላህ ጋር አምላክ አድርጎ ወይም ተመላኪ አድርጎ መያዝ ማለት አለ መሆኑን፣
3. ኢስላም አስተማሪንና ተማሪን፣ መሪንና ተመሪን በሙብት ደረጃ በእኩልነት የሚያይ መሆኑን፣
4. የዚያች መፅሐፍ ሲደርሳት ባመነችው ንግስ ቢልቂስንና የአላህ ቁርኣን ደርሷቸው አናምንም ባሉ ከሓዲያን መካከል ያለው ሰፊ ልዩነት፣

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَآ إِلَىٰ ثَمُودَ أَخَاهُمۡ صَٰلِحًا أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ فَإِذَا هُمۡ فَرِيقَانِ يَخۡتَصِمُونَ ﴿٤٥﴾ قَالَ
يَٰقَوۡمِ لِمَ تَسۡتَعۡجِلُونَ بِٱلسَّيِّئَةِ قَبۡلَ ٱلۡحَسَنَةِۖ لَوۡلَا تَسۡتَغۡفِرُونَ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ﴿٤٦﴾

**45-46.** ወደ ሰሙድም ወንድማቸውን ሷሊህን አላህን ተገዙ በማለት በእርግጥ ላክነው፡፡ ወዲያውም እነርሱ የሚነታረኩ ሁለት ጭፍሮች ሆኑ፡፡ ሕዝቦቼ ሆይ፣ ከመልካሙ በፊት በክፉው ቅጣትን አምጣብን በማለት ለምን ታስቸኩላላችሁ ይታዘንላችሁ ዘንድ አላህን ምህረትን አትለምኑምን አላቸው፡፡

قَالُواْ ٱطَّيَّرۡنَا بِكَ وَبِمَن مَّعَكَۚ قَالَ طَٰٓئِرُكُمۡ عِندَ ٱللَّهِۖ بَلۡ أَنتُمۡ قَوۡمٞ تُفۡتَنُونَ ﴿٤٧﴾ وَكَانَ فِي
ٱلۡمَدِينَةِ تِسۡعَةُ رَهۡطٖ يُفۡسِدُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا يُصۡلِحُونَ ﴿٤٨﴾ قَالُواْ تَقَاسَمُواْ بِٱللَّهِ لَنُبَيِّتَنَّهُۥ
وَأَهۡلَهُۥ ثُمَّ لَنَقُولَنَّ لِوَلِيِّهِۦ مَا شَهِدۡنَا مَهۡلِكَ أَهۡلِهِۦ وَإِنَّا لَصَٰدِقُونَ ﴿٤٩﴾

**47-49.** በአንተና ከአንተም ጋር ባሉት ሰዎች ምክንያት ገደ ቢሶች ሆን አሉት፡፡ ገደ ቢስነታችሁ አላህ ዘንድ ነው፡፡ ይልቁንም እናንተ የምትፈተኑ ህዝቦች ናችሁ አላቸው፡፡ በከተማይቱም ውስጥ በምድር የሚያበላሹና የማያሳምሩ ዘጠኝ ሰዎች ነበሩ፡፡ (ዘጠኞቹም) እርሱንና ቤተሰቡን ሌሊት እንግደልና ከዚያም ለዘመዱ የቤተሰቡን መገደላቸውን አላየንም፡፡ እኛም እውነተኞች ነን ልንል በአላህ እንማማል አሉ፡፡

وَمَكَرُواْ مَكۡرٗا وَمَكَرۡنَا مَكۡرٗا وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ﴿٥٠﴾ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ مَكۡرِهِمۡ أَنَّا
دَمَّرۡنَٰهُمۡ وَقَوۡمَهُمۡ أَجۡمَعِينَ ﴿٥١﴾ فَتِلۡكَ بُيُوتُهُمۡ خَاوِيَةَۢ بِمَا ظَلَمُوٓاْۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّقَوۡمٖ
يَعۡلَمُونَ ﴿٥٢﴾ وَأَنجَيۡنَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَكَانُواْ يَتَّقُونَ ﴿٥٣﴾

**50-53.** ተንኮልንም መከሩ፡፡ እነርሱም የማያውቁ ሲሆኑ በተንኮላቸው ምክኒያት አጠፋናቸው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የተንኮላቸውም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ እኛ እነርሱንም ሕዝቦቻቸውን በሙሉ እንዴት እንዳጠፋናቸው ተመልከት፡፡ በበደላቸው ምክንያት ባዶዎች ሲሆኑ እነዚህም ቤቶቻቸው ናቸው፡፡ በዚህም ውስጥ ለሚያውቁ ህዝቦች ሁሉ አስደናቂ ተዐምር አለበት፡፡ እነዚያንም ያመኑትንና ከክህደት ይጠነቀቁ የነበሩትን አዳንን፡፡

وَلُوطًا إِذۡ قَالَ لِقَوۡمِهِۦٓ أَتَأۡتُونَ ٱلۡفَٰحِشَةَ وَأَنتُمۡ تُبۡصِرُونَ ﴿٥٤﴾ أَئِنَّكُمۡ لَتَأۡتُونَ ٱلرِّجَالَ شَهۡوَةٗ
مِّن دُونِ ٱلنِّسَآءِۚ بَلۡ أَنتُمۡ قَوۡمٞ تَجۡهَلُونَ ﴿٥٥﴾

**54-55.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሉጥንም ለህዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። እናንተ የምታዩ ስትሆኑ መጥፎን ነገር ትሠራላችሁን? እናንተ ከሴቶች አልፋችሁ ወንዶችን ለመከጀል ትመጣላችሁን? በእውነቱ እናንተ የምትሳሳቱ ህዝቦች ናችሁ በላቸው።

**ከጉንዳኗ ምዕራፉ ከአንቀፅ (45-55) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሰሙዶች ነብዩ ሷሊህንና ተከታዮቻቸዉን ለመግደል እንዳሴሩ ሁሉ ቁረይሾችም ነቢዩን ሙሐመድን (ﷺ) ለመግደል፤ ዳዕዋቸውን ለማደናቀፍ ብዙ ተንኮሎችን አሲረው እንደነበር፤
2. ያለፉትን ነብያት ከእነኛ ሀይለኞች ጠላቶቻቸው ነፃ እንዳወጣቸው ሁሉ ነብዩንም (ﷺ) ከጠላቶቻቸው ነፃ እንደሚያወጣቸው ቃል መግባቱን፤
3. ቁርአናዊ ትረካዎች ሰዎችን ለማስተማርና እራስን ለማስተካከል ከሁሉም የሚቀድሙ መሆናቸውን፤
4. የግብረሰዶም ተግባር አስቀያሚና ፀያፍ ተግባር መሆኑን፤
5. ሸሪዓዊ ጋብቻ አማራጭ የሌለው የስሜት ማስተንፈሻ መፍትሄ መሆኑን፤

۞فَمَا كَانَ جَوَابَ قَوۡمِهِۦٓ إِلَّآ أَن قَالُوٓاْ أَخۡرِجُوٓاْ ءَالَ لُوطٖ مِّن قَرۡيَتِكُمۡۖ إِنَّهُمۡ أُنَاسٞ يَتَطَهَّرُونَ ﴿٥٦﴾ فَأَنجَيۡنَٰهُ وَأَهۡلَهُۥٓ إِلَّا ٱمۡرَأَتَهُۥ قَدَّرۡنَٰهَا مِنَ ٱلۡغَٰبِرِينَ ﴿٥٧﴾ وَأَمۡطَرۡنَا عَلَيۡهِم مَّطَرٗاۖ فَسَآءَ مَطَرُ ٱلۡمُنذَرِينَ ﴿٥٨﴾

**56-58.** የህዝቦቹም መልስ የሉጥን ቤተሰቦች ከከተማችሁ አውጡ። እነርሱ የሚጥራሩ ሰዎች ናቸውና ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም። እርሱንና ቤተሰቦቹንም አዳንን። ሚስቱ ብቻ ስትቀር። እሷማ በጥፋቱ ውስጥ ከቀሪዎቹ አደረግናት። በእነርሱም ላይ የድንጋይ ዝናብን አዘነብንባቸው። የተስፈራሪዎቹም የቅጣት ዝናም ከፋ።

قُلِ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ وَسَلَٰمٌ عَلَىٰ عِبَادِهِ ٱلَّذِينَ ٱصۡطَفَىٰٓۗ ءَآللَّهُ خَيۡرٌ أَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿٥٩﴾

**59.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)፡- ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባው። በእነዚያም በመረጣቸው ባሮቹ ላይ ሁልጊዜም ሰላም ይውረድ። አላህ በላጭ ነውን? ወይስ ያ በእርሱ የሚያጋሩት?✷ ጣዖት በል።

✷ (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «እነዚህ ሶስት ነገሮች ያለው በእርግጥ የእምነትን ጥፍጥና አግኝቷል፡-

1. አላህና መልዕክተኛው ከእርሱ ዘንድ ከማንም በላይ ተወዳጅ የሆኑ፤
2. አንድን ሰው ለአላህ ሲል ብቻ የወደደ እንደሆነ፤
3. ወደ እሳት መወርወርን እንደሚጠላ ሁሉ ወደ ኩፍር መመለስን የሚጠላ ከሆነ።»

(ለ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት በአንድ ወቅት ነብዩ (ﷺ) «በአላህ ዘንድ ከስራዎች ሁሉ በላጭ የሆነው የቱ ነው?» ተብለው ሲጠየቁ «በአላህ ማመን ነው» አሉ። «ከዚያስ?» ተባሉ «በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግል» አሉ። ለሶስተኛ ጊዜ «ከዚያስ?» ተባሉ «በአላህ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ ሐጅ ነው» በማለት መለሱ።

በዚህ ነብያዊ ሐዲስ መልዕክት በአላህ ተቀባይነት ያለውን ሐጅ መፈፀም ማለት በህላል በተገኘ ገንዘብ ቅደም ተከተሎቹ ሳይዛነፉና መስፈርቶቹ በተገቢው ተሟልተው የተፈፀመ የሐጅ ሥነ. ሥርዓት ነው።

(ሐ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «እነዚያ ያመኑና እምነታቸውን በበደል ያልቀላቀሉ እነዚያ ለነርሱ ፀጥታ አላቸው። እነርሱም የተመሩ ናቸው» (የእስሳት ምእራፍ፡ 82) የሚለው የቁርአን አንቀፅ ሲወርድ ሶሓባዎች እንዲህ አሉ፡- «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከኛ መካከል ማን ነው በደልን ያልፈፀመ?» ሲሉ ጠየቋቸው። ይህን ጊዜ አላህ «ሉቅማን ለልጁ እርሱ የሚገሰፀው ሲሆን፤ ልጄ ሆይ! በአላህ አምልኮ ላይ ጣኦትን አታጋራ ታላቅ በደል ነውና» የሚለው የቁርአን አንቀፅ ለሶሓቦች ምላሽ ይሆን ዘንድ ወረደ።

أَمَّنۡ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَأَنزَلَ لَكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَنۢبَتۡنَا بِهِۦ حَدَآئِقَ ذَاتَ بَهۡجَةٖ مَّا كَانَ لَكُمۡ أَن تُنۢبِتُواْ شَجَرَهَآۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ بَلۡ هُمۡ قَوۡمٞ يَعۡدِلُونَ ٦٠

**60.** ወይም ያ! ሰማያትንና ምድርን የፈጠረና ከሰማይም ለእናንተ ውሃን ያወረደው? ይበልጣል? ወይስ ያ የሚያጋሩት በእርሱም ባለውበት የሆኑትን የታጠሩ አትክልቶችን ዛፍዋን ልታበቅሉ ለእናንተ ችሎታ ሳይኖራችሁ እኛ ብቻችንን አበቀልን። ከአላህ ጋር ሌላ ትክክለኛ አምላክ አለን? (የለም) ግን እነርሱ ከእውነት የሚያዘነብሉ ህዝቦች ናቸው።

أَمَّن جَعَلَ ٱلۡأَرۡضَ قَرَارٗا وَجَعَلَ خِلَٰلَهَآ أَنۡهَٰرٗا وَجَعَلَ لَهَا رَوَٰسِيَ وَجَعَلَ بَيۡنَ ٱلۡبَحۡرَيۡنِ حَاجِزًاۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ٦١

**61.** (ሰዎች ሆይ!) ወይም ያ! ምድርን መርጊያ ያደረገና በመካከሏም ወንዞችን ያደረገ ለእርሷም ጋራዎችን ያደረገ (በጣፋጩና በጨዋማው) በሁለቱ ባህሮችም መካከል ግርዶን ያደረገ ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት? ከአላህ ጋር ሌላ አምላክ አለን? ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።

أَمَّن يُجِيبُ ٱلۡمُضۡطَرَّ إِذَا دَعَاهُ وَيَكۡشِفُ ٱلسُّوٓءَ وَيَجۡعَلُكُمۡ خُلَفَآءَ ٱلۡأَرۡضِۗ أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قَلِيلٗا مَّا تَذَكَّرُونَ ٦٢

**62.** ወይም ያ! ችግረኛን በለመነው ጊዜ የሚቀበል መከራንም የሚያስወግድ በምድርም ላይ ምትኮች የሚያደርጋችሁ ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት? ከአላህ ጋር ሌላ ትክክለኛ አምላክ አለን? ጥቂትንም አትገሰፁም።

أَمَّن يَهۡدِيكُمۡ فِي ظُلُمَٰتِ ٱلۡبَرِّ وَٱلۡبَحۡرِ وَمَن يُرۡسِلُ ٱلرِّيَٰحَ بُشۡرَۢا بَيۡنَ يَدَيۡ رَحۡمَتِهِۦٓۗ
أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ تَعَٰلَى ٱللَّهُ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٦٣

**63.** ወይም ያ! በየብስና በባህር ጨለማዎች ውስጥ የሚመራችሁ ነፋሶችንም ከዝናሙ በፊት አብሳሪ ሆነው የሚልክ ይበልጣልን? ወይስ ከነሱ ከአላህ ጋር የሚያጋሩት? ከአላህ ጋር ሌላ ትክክለኛ አምላክ አለን? አላህ በእርሱ ከሚያጋሯቸው ነገሮች ሁሉ ላቀ።

**ከጉንዳኗ ምዕራፉ ከአንቀፅ (56-63) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በነብያት ላይ ማደምና ከሀገር እንዲወጡ ማሴር የቀደምት ከሓዲያን ፈለግ እንደነበርና ከሀገር መባረር በነብዩ (ﷺ) የተጀመረ እንዳልሆነ፤
2. በሁሉ ነገር ላይ የሚታየው ሁኔታ ሁሉ የአላህን አንድነት የሚያመለክት በመሆኑና በአንድነቱ ሁሉም ነገር የሚመሰክር መሆኑን፤
3. ሰዎችን ለማሳመንና የማያውቁትን ነገር ለማስረዳት ዉይይት ከፍተኛ መሳሪያ መሆኑን፤
4. የቁርአን ተአምርና ድሮ በቁርአን ተጠቁመው እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ያልተደረሰባቸው ብዙ ነገሮች መኖራቸውን፤
5. የተፈጥሮን ውበት ማንም ሊወዳደራት የማይችል ተዐምር እንዳላት እንማራለን።

أَمَّن يَبۡدَؤُاْ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ وَمَن يَرۡزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِۗ
أَءِلَٰهٞ مَّعَ ٱللَّهِۚ قُلۡ هَاتُواْ بُرۡهَٰنَكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٦٤

**64.** ወይም ያ! መፍጠርን የሚጀምር ከዚያ የሚመልሰው ከሰማይና ከምድርም ሲሳይን የሚሰጣችሁ አምላክ ይበልጣልን? ወይስ የሚያጋሩት? ከአላህ ጋር ሌላ ትክክለኛ አምላክ አለን? እውነተኞች እንደሆናችሁ አስረጃችሁን አምጡ በላቸው።

قُل لَّا يَعۡلَمُ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ ٱلۡغَيۡبَ إِلَّا ٱللَّهُۚ وَمَا يَشۡعُرُونَ أَيَّانَ يُبۡعَثُونَ ٦٥ بَلِ
ٱدَّٰرَكَ عِلۡمُهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِۚ بَلۡ هُمۡ فِي شَكّٖ مِّنۡهَاۖ بَلۡ هُم مِّنۡهَا عَمُونَ ٦٦

**65-66.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ ሩቅን ምስጢር አያውቅም። አላህ ግን ያውቀዋል። መቼ እንደሚቀሰቀሱም አያውቁም በላቸው። በእውነት የመጨረሻይቱን ዓለም ሁኔታ ማወቃቸው ተሟላን? አይደለም እነርሱ ከእርሷ በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። በእውነትም እነርሱ ከእርሷ እውሮች ናቸው።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَءِذَا كُنَّا تُرَٰبًا وَءَابَآؤُنَآ أَئِنَّا لَمُخۡرَجُونَ ٦٧
لَقَدۡ وُعِدۡنَا هَٰذَا نَحۡنُ وَءَابَآؤُنَا مِن قَبۡلُ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّآ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ٦٨

**67-68.** እነዚያም በአላህ የካዱት አሉ፡- እኛም አባቶቻችንም ዐፈር በሆንን ጊዜ እንደ ገና ከመቃብር የምንወጣ ነን? ይህንን እኛም ሆነ ከእኛ በፊት የነበሩት አባቶቻችን በእርግጥ ተቀጥረንበታል። ይህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች እንጂ ሌላ አይደለም አሉ።

قُلۡ سِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَٱنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ٦٩

**69.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ላይ ሂዱ የአመፀኞችም መጨረሻ እንዴት እንደነበረ ተመልከቱ በላቸው።

وَلَا تَحۡزَنۡ عَلَيۡهِمۡ وَلَا تَكُن فِي ضَيۡقٖ مِّمَّا يَمۡكُرُونَ ٧٠

**70.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእነርሱም ላይ አትዘን። ከሚመክሩብህም ነገር በጭንቀት ውስጥ አትሁን።

وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلۡوَعۡدُ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٧١
قُلۡ عَسَىٰٓ أَن يَكُونَ رَدِفَ لَكُم بَعۡضُ ٱلَّذِي تَسۡتَعۡجِلُونَ ٧٢

**71-72.** እውነተኞችም እንደሆናችሁ ይህ ቀጠሮ መቼ ነው? ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዚያ የምትቻኮሉበት ከፊሉ ለእናንተ የቀረበ መሆኑ ተረጋግጧል በላቸው።

وَإِنَّ رَبَّكَ لَذُو فَضۡلٍ عَلَى ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَهُمۡ لَا يَشۡكُرُونَ ٧٣

**73.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም በሰዎች ላይ በእርግጥ የችሮታ ባለቤት ነው። ግን አብዛኞዎቻቸው አያመሰግኑም።

وَإِنَّ رَبَّكَ لَيَعۡلَمُ مَا تُكِنُّ صُدُورُهُمۡ وَمَا يُعۡلِنُونَ ٧٤
وَمَا مِنۡ غَآئِبَةٖ فِي ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِ إِلَّا فِي كِتَٰبٖ مُّبِينٍ ٧٥

**74-75.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም ልቦቻቸው የሚደብቁትንና የሚገልፁትን ያውቃል። በሰማይም ሆነ በምድር ውስጥ ምንም የተደበቀ ነገር የለም። ገላጭ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ ያለ ቢሆን እንጂ።

إِنَّ هَٰذَا ٱلْقُرْءَانَ يَقُصُّ عَلَىٰ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ أَكْثَرَ ٱلَّذِى هُمْ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ﴿٧٦﴾ وَإِنَّهُۥ لَهُدًى
وَرَحْمَةٌ لِّلْمُؤْمِنِينَ ﴿٧٧﴾ إِنَّ رَبَّكَ يَقْضِى بَيْنَهُم بِحُكْمِهِۦ ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٧٨﴾

**76-78.** ይህ ቁርኣን እነዚያ የኢስራኤል ልጆች እነርሱ በእርሱ ላይ የሚለያዩበትን ጉዳይ አብዛኛውን ይነግራል። እርሱም ለምዕመናን ብቸኛ መምሪያና እዝነት ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ በመካከላቸው በትክክል ፍርዱ ይፈርዳል እርሱም አሸናፊና ዐዋቂ ነው።

**ከጉንዳኗ ምዕራፍ ከአንቀፅ (64-76) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የአላህን ተዐምሮች መዘርዘር፤
2. ሰዎች ይህን ሁሉ ተዐምር እያዩ ክህደት ዉስጥ መግባታቸው ሞኝነት እንደሆነ መጠቆም፤
3. ከሓዲያን በምድር ላይ እየተጓዙ የመሰሎቻቸው ውድቀትምን ይመስል እንደነበር መጠቆም፤

ነብዩ (ﷺ) ከሓዲያን በሚያደርጉት ሁሉ መበሳጨት እንደሌለባቸው ማፅናናት።

فَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِ ۖ إِنَّكَ عَلَى ٱلْحَقِّ ٱلْمُبِينِ ﴿٧٩﴾ إِنَّكَ لَا تُسْمِعُ ٱلْمَوْتَىٰ وَلَا تُسْمِعُ ٱلصُّمَّ ٱلدُّعَآءَ
إِذَا وَلَّوْا۟ مُدْبِرِينَ ﴿٨٠﴾ وَمَآ أَنتَ بِهَٰدِى ٱلْعُمْىِ عَن ضَلَٰلَتِهِمْ ۖ إِن تُسْمِعُ إِلَّا مَن يُؤْمِنُ
بِـَٔايَٰتِنَا فَهُم مُّسْلِمُونَ ﴿٨١﴾

**79-81.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ላይ ተጠጋ። አንተ ግልጽ በሆነው እውነት ላይ ነህና። መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! አንተ ሙታንን አታሰማም። ደንቆሮዎችንም የሚተው ሆነው በዞሩ ጊዜ ጥሪን አታሰማም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተም ልበ ዕውሮችን ከጥመታቸው አቅኚ አይደለህም። እነዚያን በአንቀፆቻችን በትክክል የሚይምኑትን እንጂ አታሰማም። እነርሱ ፍፁም ታዛዥች ናቸውና።

۞ وَإِذَا وَقَعَ ٱلْقَوْلُ عَلَيْهِمْ أَخْرَجْنَا لَهُمْ دَآبَّةً مِّنَ ٱلْأَرْضِ تُكَلِّمُهُمْ
أَنَّ ٱلنَّاسَ كَانُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا لَا يُوقِنُونَ ﴿٨٢﴾

**82.** በእነርሱም ላይ የቅጣት ቃሉ* በተረጋገጠ ጊዜ ሰዎቹ በአንቀፆቻችን የማያረጋግጡ እንደነበሩ የምትነግራቸውን እንስሳ ከምድር እናወጣላቸዋለን።

* ቅጣቱ፤ ውሳኔው. ቀጠሮው ማለት ሊሆን እንደሚችል ሀሳባቸውን የሰጡ ምሁራን ቢኖሩም የተመረጠው ቅጣቱ ማለት ነው የሚለው ነው።

وَيَوۡمَ نَحۡشُرُ مِن كُلِّ أُمَّةٖ فَوۡجٗا مِّمَّن يُكَذِّبُ بِـَٔايَٰتِنَا فَهُمۡ يُوزَعُونَ ﴿٨٣﴾
حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءُو قَالَ أَكَذَّبۡتُم بِـَٔايَٰتِي وَلَمۡ تُحِيطُواْ بِهَا عِلۡمًا أَمَّاذَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٨٤﴾
وَوَقَعَ ٱلۡقَوۡلُ عَلَيۡهِم بِمَا ظَلَمُواْ فَهُمۡ لَا يَنطِقُونَ ﴿٨٥﴾ أَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّا جَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ لِيَسۡكُنُواْ
فِيهِ وَٱلنَّهَارَ مُبۡصِرًاۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ﴿٨٦﴾

**83-86.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሕዝቦቹም ሁሉ በአንቀፆች የሚያስተባብሉትን ጭፍሮች የምንሰበስብበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ እነርሱም ይከመከማሉ፡፡ በመጡም ጊዜ (አላህ) ይላቸዋል፡ በአንቀጾቼ እርሷን በማወቅ ያላዳረሳችሁ ስትሆኑ አስተባበላችሁን? ወይስ ምን ትሰሩ ነበራችሁ?፡፡ በመበደላቸውም ምክኒያት በእነርሱ ላይ ቃሉ ይፈፀምባቸዋል፡፡ እነርሱም አይናገሩም፡፡ እኛ ሌሊትን በእርሱ ውስጥ እንደሚያርፉበት ቀንንም የሚያሳይ እንዳደረግን አያዩምን? ለሚያምኑ ሕዝቦች በዚህ ውስጥ ተዐምራቶች አሉበት፡፡

وَيَوۡمَ يُنفَخُ فِي ٱلصُّورِ فَفَزِعَ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ
إِلَّا مَن شَآءَ ٱللَّهُۚ وَكُلٌّ أَتَوۡهُ دَٰخِرِينَ ﴿٨٧﴾

**87.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በቀንዱም በሚነፋ ቀን በሰማያት ውስጥ ያሉትና በምድርም ውስጥ ያሉት ሁሉ አላህ የሻው ነገር ብቻ ሲቀር በሚደነግጡ ጊዜ የሚኾነውን አስታውስ ሁሉም የተናነሱ ኾነውም ወደ እርሱ ይመጣሉ፡፡

وَتَرَى ٱلۡجِبَالَ تَحۡسَبُهَا جَامِدَةٗ وَهِيَ تَمُرُّ مَرَّ ٱلسَّحَابِۚ
صُنۡعَ ٱللَّهِ ٱلَّذِيٓ أَتۡقَنَ كُلَّ شَيۡءٍۚ إِنَّهُۥ خَبِيرُۢ بِمَا تَفۡعَلُونَ ﴿٨٨﴾

**88.** ጋራዎችንም እርሷ እንደ ደመና አስተላለፍ የምታልፍ ስትኾን የቆመች ናት ብለህ የምታስባት ኾና ታያለህ የዚያን ነገሩን ሁሉ ያጠነከረውን የአላህን ጥበብ ተመልከት እርሱ በምትሠሩት ሁሉ ውስጥ ዐዋቂ ነው፡፡

مَن جَآءَ بِٱلۡحَسَنَةِ فَلَهُۥ خَيۡرٞ مِّنۡهَا وَهُم مِّن فَزَعٖ يَوۡمَئِذٍ ءَامِنُونَ ﴿٨٩﴾

**89.** መልካም ሥራን የሰራ ሰው ለእርሱ ከእርሷ የበለጠ ምንዳ አለው፡፡ እነርሱም በዚያ ቀን ከድንጋጤ ነፃ ናቸው፡፡

وَمَن جَآءَ بِٱلسَّيِّئَةِ فَكُبَّتۡ وُجُوهُهُمۡ فِي ٱلنَّارِ هَلۡ تُجۡزَوۡنَ إِلَّا مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٩٠﴾

**90.** መጥፎንም የሰሩ ሰዎች ፊቶቻቸው በእሳት ውስጥ ይደፋሉ። ትሠሩት የነበራችሁትን እንጂ አትመነዱም (ይባላሉ)።

إِنَّمَآ أُمِرۡتُ أَنۡ أَعۡبُدَ رَبَّ هَٰذِهِ ٱلۡبَلۡدَةِ ٱلَّذِي حَرَّمَهَا وَلَهُۥ كُلُّ شَيۡءٖۖ
وَأُمِرۡتُ أَنۡ أَكُونَ مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ﴿٩١﴾ وَأَنۡ أَتۡلُوَاْ ٱلۡقُرۡءَانَۖ فَمَنِ ٱهۡتَدَىٰ
فَإِنَّمَا يَهۡتَدِي لِنَفۡسِهِۦۖ وَمَن ضَلَّ فَقُلۡ إِنَّمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلۡمُنذِرِينَ ﴿٩٢﴾
وَقُلِ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ سَيُرِيكُمۡ ءَايَٰتِهِۦ فَتَعۡرِفُونَهَاۚ وَمَا رَبُّكَ بِغَٰفِلٍ عَمَّا تَعۡمَلُونَ ﴿٩٣﴾

**91-93.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የታዘዝኩት የዚህችን አገር የመካን ጌታ ያንን ክልክል ያደረጋትን አላህን እንድገዛ ብቻ ነው። ነገሩም ሁሉ የእርሱ ነው። ከሙስሊሞችም* እንድሆን ታዝዣለሁ በላቸው። ቁርአንንም እንዳነብ ታዝዣለሁ። በቀጥተኛው መንገድ የተመራ ሰው ሁሉ የሚመራው ለራሱ ብቻ ነው። የተሳሳተም ሰው እኔ ከአስፈራሪዎች ነኝ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምስጋና ሁሉ ለአላህ ብቻ ነው። ተአምራትን ወደ ፊት ያሳያችኋል። ታውቋትምአላችሁ በላቸው። ጌታህም ከምትሠሩት ሁሉ ዘንጊ አይደለም።

✷ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላለፉት«መካ ሲከፈት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አላህ ይህችን ከተማ የተጠበቀች አድርጓታል። ስለዚህ እሾሃማ ጫካዎቿን መቁረጥ የለባችሁም። ደኖቿ መደፈር የለባቸውም። ውዳቂ ነገሮቿ እንኳ በአደባባይ እንዲነሳ እስካልታወጀ ድረስ አንዱ ሰው ማንሳት የለበትም።»

### ከጉንደኗ ከ (77-93) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፦

1. ወደ ቀናው መንገድ መምራት የአላህ ብቸኛ ስልጣን መሆኑን፤
2. በአላህ ላይ መመካት ማለት ምክንያቶቹን ከመፈፀመም ጋራ መሆኑን፤
3. የትንሳኤ ቀን ለመድረሱ ብዙ ምልክቶች እንዳሉና ከነዚህም መካከል አንዱ ሰዎችን የምታናግር እንስሳ ከምድር መውጣቷ መሆኑን፤
4. የመልካም ስራ ክፍያ እጥፍ ድርብ መሆኑን፤
5. ነብዩ (ﷺ) ከማስፈራራት ያለፉ ኃላፊነት የሌለባቸው መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የጉንዳኗ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (28)
# የታሪኮች ምዕራፍ ነው።
# (ሱረቱ አል ቀሶስ)

سُورَةُ القَصَصِ

## በመካ የወረደ ሲሆን አናቅፁ (88) ናቸው።
## የሱረቱ አል ቀሰስ መግቢያ

በአን-ነምል ምዕራፍ ውስጥ ጠቅለል ባለ መልኩ ስለተወሳው የነቢዩ ሙሳና የፊርኣውን ታሪክ በዝርዝር ያወሳል። ሙሳ ከመወለዳቸው አንስቶ ያለፈባቸውን መከራ ከዚያ ከፊርዓውን ጋር ያሳለፉት ትግል ሁሉ ያነሳል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

طسٓمٓ ١

**1.** ጧ፤ ሲን፤ ሚይም፤*

✶ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርአን ታአምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)፡፡

تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡمُبِينِ ٢

**2.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኒህ ገላጭ ከሆነው መጽሐፍ አንቀፆች ናቸው፡፡

نَتۡلُواْ عَلَيۡكَ مِن نَّبَإِ مُوسَىٰ وَفِرۡعَوۡنَ بِٱلۡحَقِّ لِقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ٣ إِنَّ فِرۡعَوۡنَ عَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِ
وَجَعَلَ أَهۡلَهَا شِيَعٗا يَسۡتَضۡعِفُ طَآئِفَةٗ مِّنۡهُمۡ يُذَبِّحُ أَبۡنَآءَهُمۡ وَيَسۡتَحۡيِۦ نِسَآءَهُمۡۚ إِنَّهُۥ كَانَ
مِنَ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٤ وَنُرِيدُ أَن نَّمُنَّ عَلَى ٱلَّذِينَ ٱسۡتُضۡعِفُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَنَجۡعَلَهُمۡ أَئِمَّةٗ
وَنَجۡعَلَهُمُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ٥ وَنُمَكِّنَ لَهُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَنُرِيَ فِرۡعَوۡنَ وَهَٰمَٰنَ وَجُنُودَهُمَا مِنۡهُم
مَّا كَانُواْ يَحۡذَرُونَ ٦

**3-6.** ከሙሳና ከፈርኦን ዜና እውነተኞች ስንሆን ለሚያምኑ ህዝቦች በአንተ ላይ እናነባለን፡፡ ፈርዖን በምድር ላይ ተንበጣረረ፡፡ ነዋሪዎችዋንም የተከፋፈሉ ጓዶች አደረጋቸው፡፡ ከእነርሱ ጭፍሮችን ያዳክማል፡፡ ወንዶች ልጆቻቸውን በብዛት ያርዳል፡፡ ሴቶቻቸውንም ይተዋል፤ እርሱ ከሚያበላሹት ሰዎች ነበርና፡፡ በእነዚያ በምድር ውስጥ በተጨቆኑት ላይ ልንለግስ መሪዎችም ልናደርጋቸው ወራሾችም ልናደርጋቸው እንሻለን፡፡ ለእነርሱም በምድር ላይ ልናስመች ፈርዖንንና ሃማንንም ሰራዊቶቻቸውንም ከእነርሱ ይፈሩት የነበሩትን ነገር ልናሳያቸው እንሻለን፡፡

وَأَوۡحَيۡنَآ إِلَىٰٓ أُمِّ مُوسَىٰٓ أَنۡ أَرۡضِعِيهِۖ فَإِذَا خِفۡتِ عَلَيۡهِ فَأَلۡقِيهِ فِي ٱلۡيَمِّ وَلَا تَخَافِي وَلَا تَحۡزَنِيٓۖ
إِنَّا رَآدُّوهُ إِلَيۡكِ وَجَاعِلُوهُ مِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ٧ فَٱلۡتَقَطَهُۥٓ ءَالُ فِرۡعَوۡنَ لِيَكُونَ لَهُمۡ عَدُوّٗا

وَحَزَنًاۗ إِنَّ فِرۡعَوۡنَ وَهَٰمَٰنَ وَجُنُودَهُمَا كَانُواْ خَٰطِـِٔينَ ٨ وَقَالَتِ ٱمۡرَأَتُ فِرۡعَوۡنَ قُرَّتُ عَيۡنٖ
لِّي وَلَكَۖ لَا تَقۡتُلُوهُ عَسَىٰٓ أَن يَنفَعَنَآ أَوۡ نَتَّخِذَهُۥ وَلَدٗا وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ٩

**7-9.** ወደ ሙሳም እናት አጥቢው፤ በእርሱም ላይ በፈራሽ ጊዜ በባህሩ ውስጥ ጣይው፤ አትፍሪም። አትዘኝም። እኛ ወዳንቺ መላሾቹና ከመልእክተኞቹም አድራጊዎቹ ነንና ማለትን አመለከትን (አወረድን)። የፈርዖን ቤተሰቦችም መጨረሻው ለእነርሱ ጠላት ሐዘንም ይሆን ዘንድ አነሱት። ፈርዖንና ሃማንም ሰራዊቶቻቸውም ኃጢአተኞች ነበሩ። የፈርዖንም ሚስት* ለእኔ ሆነ ለአንተ የዓይናችን መርጊያ ነው። አትግደሉት፤ ሊጠቅመን ወይም ልጅ አድርገን ልንይዘው ይከጀላልና አለች፤ እነርሱም ፍጻሜውን የማያውቁ ሆነው አነሱት።

✳ እኒህ ሴት ኣስያ ቢንቱ ሙዛሂም ይባለሉ።

وَأَصۡبَحَ فُؤَادُ أُمِّ مُوسَىٰ فَٰرِغًاۖ إِن كَادَتۡ لَتُبۡدِي بِهِۦ لَوۡلَآ أَن رَّبَطۡنَا عَلَىٰ قَلۡبِهَا لِتَكُونَ
مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١٠ وَقَالَتۡ لِأُخۡتِهِۦ قُصِّيهِۖ فَبَصُرَتۡ بِهِۦ عَن جُنُبٖ وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ١١
۞وَحَرَّمۡنَا عَلَيۡهِ ٱلۡمَرَاضِعَ مِن قَبۡلُ فَقَالَتۡ هَلۡ أَدُلُّكُمۡ عَلَىٰٓ أَهۡلِ بَيۡتٖ يَكۡفُلُونَهُۥ لَكُمۡ
وَهُمۡ لَهُۥ نَٰصِحُونَ ١٢ فَرَدَدۡنَٰهُ إِلَىٰٓ أُمِّهِۦ كَيۡ تَقَرَّ عَيۡنُهَا وَلَا تَحۡزَنَ وَلِتَعۡلَمَ أَنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ
حَقّٞ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ١٣

**10-13.** የሙሳም እናት ልብ ባዶ ሆነ። ከምዕመናን ትሆን ዘንድ በልቧ ላይ ባላጠነከርን ኖሮ ልትገልፀው ቀርባ ነበር። ለእህቱም ተከታተይው አለቻት። እርሱንም እነርሱ የማያውቁ ሲሆን በሩቅ ሆና አየችው፤ ወደ እናቱ ከመመለሱ በፊትም አጥቢዎችን መጥባትን በእርሱ ላይ እርም አደረግን። እህቱም ለእናንተ የሚያሳድግላችሁን እነርሱም ለእርሱ ቅን አገልጋዮች የሆኑን ቤተሰቦች ላመልክታችሁን? አለችም። ወደ እናቱም ዓይንዋ እንድትረጋ እንዳታዝንም የአላህም የተስፋ ቃል እርግጥ መሆኑን እንድታውቅ መለስነው። ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።

وَلَمَّا بَلَغَ أَشُدَّهُۥ وَٱسۡتَوَىٰٓ ءَاتَيۡنَٰهُ حُكۡمٗا وَعِلۡمٗاۚ وَكَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٤

**14.** ብርታቷንም በደረሰና በተስተካከለ ጊዜ ጥበብንና እውቀትን ሰጠነው፤ እንደዚሁም መልካም ሰሪዎችን እንመነዳለን።

وَدَخَلَ ٱلْمَدِينَةَ عَلَىٰ حِينِ غَفْلَةٍ مِّنْ أَهْلِهَا فَوَجَدَ فِيهَا رَجُلَيْنِ يَقْتَتِلَانِ هَٰذَا مِن شِيعَتِهِۦ
وَهَٰذَا مِنْ عَدُوِّهِۦ ۖ فَٱسْتَغَٰثَهُ ٱلَّذِى مِن شِيعَتِهِۦ عَلَى ٱلَّذِى مِنْ عَدُوِّهِۦ فَوَكَزَهُۥ مُوسَىٰ
فَقَضَىٰ عَلَيْهِ ۖ قَالَ هَٰذَا مِنْ عَمَلِ ٱلشَّيْطَٰنِ ۖ إِنَّهُۥ عَدُوٌّ مُّضِلٌّ مُّبِينٌ ﴿١٥﴾ قَالَ رَبِّ إِنِّى ظَلَمْتُ
نَفْسِى فَٱغْفِرْ لِى فَغَفَرَ لَهُۥٓ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿١٦﴾

**15-16.** ሙሳ ከተማይቱንም ሰዎቿ በዝንጋቴ ላይ ሆነው ሳሉ ገባ፡፡ በእርሷም ውስጥ የሚጋደሉን ሁለት ሰዎች አገኘ፤ ይህ (አንዱ) ከወገኑ ነው፤ ይህ (ሌላው) ደግሞ ከጠላቱ ነው፤ ያ ከወገኑ የሆነው ሰው በዚያ ከጣላት በሆነው ሰው ላይ እርዳታን ጠየቀው፤ ሙሳም በጡጫ መታው፤ ገደለውም፡፡ ይህ ከሰይጣን ስራ ነው፤ እርሱ ግልጽ አሣሣች ጠላት ነውና አለ፡፡ ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ ለኔም ማር አለ ለርሱም ምህረት አደረገለት፤ እርሱ መሓሪና አዛኙ ነውና፡፡

قَالَ رَبِّ بِمَآ أَنْعَمْتَ عَلَىَّ فَلَنْ أَكُونَ ظَهِيرًا لِّلْمُجْرِمِينَ ﴿١٧﴾

**17.** ጌታዬ ሆይ፣ በእኔ ላይ በመለገስህ ይሁንብኝ ከስህተቴ እፀፀታለሁ ለአመፀኞችም ፈጽሞ ረዳት አልሆንም አለ፡፡

فَأَصْبَحَ فِى ٱلْمَدِينَةِ خَآئِفًا يَتَرَقَّبُ فَإِذَا ٱلَّذِى ٱسْتَنصَرَهُۥ بِٱلْأَمْسِ يَسْتَصْرِخُهُۥ ۚ قَالَ لَهُۥ
مُوسَىٰٓ إِنَّكَ لَغَوِىٌّ مُّبِينٌ ﴿١٨﴾ فَلَمَّآ أَنْ أَرَادَ أَن يَبْطِشَ بِٱلَّذِى هُوَ عَدُوٌّ لَّهُمَا قَالَ يَٰمُوسَىٰٓ
أَتُرِيدُ أَن تَقْتُلَنِى كَمَا قَتَلْتَ نَفْسًۢا بِٱلْأَمْسِ ۖ إِن تُرِيدُ إِلَّآ أَن تَكُونَ جَبَّارًا فِى ٱلْأَرْضِ
وَمَا تُرِيدُ أَن تَكُونَ مِنَ ٱلْمُصْلِحِينَ ﴿١٩﴾ وَجَآءَ رَجُلٌ مِّنْ أَقْصَا ٱلْمَدِينَةِ يَسْعَىٰ قَالَ
يَٰمُوسَىٰٓ إِنَّ ٱلْمَلَأَ يَأْتَمِرُونَ بِكَ لِيَقْتُلُوكَ فَٱخْرُجْ إِنِّى لَكَ مِنَ ٱلنَّٰصِحِينَ ﴿٢٠﴾ فَخَرَجَ مِنْهَا
خَآئِفًا يَتَرَقَّبُ ۖ قَالَ رَبِّ نَجِّنِى مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢١﴾

**18-21.** በከተማይቱም ውስጥ ፈሪ የሚጠባበቅ ሆኖ አደረ፤ በንጋቱም ያ ትላንት እርዳታን የጠየቀው ሰው በጩኸት እርዳታን ይጠይቀዋል፤ ሙሳ ለእርሱ፡- አንተ በእርግጥ ግልጽ ጠማማ ነህ አለው፡፡ ሙሳ ያንን እርሱ ለሁለቱም ጠላት የሆነው ሰው በኃይል ሊይዘው በፈለገም ጊዜ ሙሳ ሆይ በትላንትናው ቀን ነፍስን እንደ ገደልክ ልትገድለኝ ትፈልጋለህን? በምድር ላይ ጨካኝ መሆንን እንጂ ሌላ አትፈልግም ከመልካም ሰሪዎች መሆንን አትፈልግም አለው፡፡ ከከተማይቱም ዳርቻ አንድ ሰው እየሮጠ መጣ

ሙሳ ሆይ! ሹማምንቶቹ ሊገድሉህ ባንተ ይመካከራሉና ውጣ እኔ ላንተ ከመካሪዎች ነኝና አለው። የፈራና የሚጠባበቅ ሆኖም ከእርሷ ወጣ፤ ጌታዬ ሆይ! ከበደለኞች ህዝቦች አድነኝ አለ።

وَلَمَّا تَوَجَّهَ تِلۡقَآءَ مَدۡيَنَ قَالَ عَسَىٰ رَبِّيٓ أَن يَهۡدِيَنِي سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ﴿٢٢﴾ وَلَمَّا وَرَدَ مَآءَ
مَدۡيَنَ وَجَدَ عَلَيۡهِ أُمَّةٗ مِّنَ ٱلنَّاسِ يَسۡقُونَ وَوَجَدَ مِن دُونِهِمُ ٱمۡرَأَتَيۡنِ تَذُودَانِۖ قَالَ مَا
خَطۡبُكُمَاۖ قَالَتَا لَا نَسۡقِي حَتَّىٰ يُصۡدِرَ ٱلرِّعَآءُۖ وَأَبُونَا شَيۡخٞ كَبِيرٞ ﴿٢٣﴾ فَسَقَىٰ لَهُمَا ثُمَّ تَوَلَّىٰٓ
إِلَى ٱلظِّلِّ فَقَالَ رَبِّ إِنِّي لِمَآ أَنزَلۡتَ إِلَيَّ مِنۡ خَيۡرٖ فَقِيرٞ ﴿٢٤﴾

**22-24.** ወደ መድየን አቅጣጫ ፊቱን ባዞረ ጊዜም ጌታዬ ቀጥተኛውን መንገድ ሊመራኝ እከጅላለሁ አለ። ወደ መድየንም ውሃ በመጣ ጊዜ እርሱ ላይ ከሰዎች ጭፍሮችን መንጋዎቻቸውን የሚያጠጡ ሆነው አገኘ፤ ከእነርሱ በታችም ከውሃው መንጎቻቸውን የሚከለክሉን ሁለት ሴቶች አገኘ። ነገራችሁ ምንድን ነው? አላቸው እረኞች ሁሉ መንጋዎቻቸውን እስከሚመልሱ አናጠጣም። አባታችንም ትልቅ ሽማግሌ ነው አሉት። ለሁለቱም አጠጣላቸው ከዚያ ወደ ጥላው ዘወር አለ ጌታዬ ሆይ! እኔ ከመልካም ነገር ወደ እኔ ለምታወርደው ፈላጊ ነኝ አለ።

فَجَآءَتۡهُ إِحۡدَىٰهُمَا تَمۡشِي عَلَى ٱسۡتِحۡيَآءٖ قَالَتۡ إِنَّ أَبِي يَدۡعُوكَ لِيَجۡزِيَكَ أَجۡرَ مَا سَقَيۡتَ لَنَاۚ
فَلَمَّا جَآءَهُۥ وَقَصَّ عَلَيۡهِ ٱلۡقَصَصَ قَالَ لَا تَخَفۡۖ نَجَوۡتَ مِنَ ٱلۡقَوۡمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٢٥﴾
قَالَتۡ إِحۡدَىٰهُمَا يَٰٓأَبَتِ ٱسۡتَـٔۡجِرۡهُۖ إِنَّ خَيۡرَ مَنِ ٱسۡتَـٔۡجَرۡتَ ٱلۡقَوِيُّ ٱلۡأَمِينُ ﴿٢٦﴾

**25-26.** ከሁለቱ አንደኛይቱም ከህፍረት ጋር የምትሄድ ሆና ወደ እርሱ መጣች፤ አባቴ ለእኛ ያጠጣህልንን ዋጋ ሊሰጥህ ይጠራሃል አለችው፤ ወደ እርሱ በመጣና ወሬውን በእርሱ ላይ በተረከለትም ጊዜ አትፍራ። ከበደለኞች ህዝቦች ድነሃል አለው። ከሁለቱ አንደኛይቱም አባቴ ሆይ ቅጠረው ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ፤ ብርቱው፤ ታማኙ ነውና አለችው።

قَالَ إِنِّيٓ أُرِيدُ أَنۡ أُنكِحَكَ إِحۡدَى ٱبۡنَتَيَّ هَٰتَيۡنِ عَلَىٰٓ أَن تَأۡجُرَنِي ثَمَٰنِيَ حِجَجٖۖ فَإِنۡ أَتۡمَمۡتَ
عَشۡرٗا فَمِنۡ عِندِكَۖ وَمَآ أُرِيدُ أَنۡ أَشُقَّ عَلَيۡكَۚ سَتَجِدُنِيٓ إِن شَآءَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٢٧﴾ قَالَ
ذَٰلِكَ بَيۡنِي وَبَيۡنَكَۖ أَيَّمَا ٱلۡأَجَلَيۡنِ قَضَيۡتُ فَلَا عُدۡوَٰنَ عَلَيَّۖ وَٱللَّهُ عَلَىٰ مَا نَقُولُ وَكِيلٞ ﴿٢٨﴾

**27-28.** ስምንትን ዓመታት ልታገለግለኝ እኔ ከእነዚህ ሁለት ሴቶች ልጆቼ አንዷቷን ላጋባህ እሻለሁ፤ ዐስርን ብትሞላም ከአንተ ነው። በአንተ ላይ ማስቸገርንም አልሻም፤ አላህ የሻ እንደሆነ ከመልካም ሰዎች ሆኜ ታገኘኛለህ አለው። ሙሳም ይህ ውሌታ በእኔና ባንተ መካከል ረጊ ነው። ከሁለት ጊዜያቶች ማንኛውንም ብፈጽም በእኔ ላይ ወሰን ማለፍ የለም። አላህ በምንለው ላይ ምስክር ነው አለ።

**ከታሪኮች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቁርኣንን ተዓምርነት ማረጋገጥ፤
2. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
3. ከግፍ በሰዎች ላይ ከመኩራት እና በመሬት ላይ ብክለትን ከማስፋፋት ማስጠንቀቅ፤
4. ሙዕሚኖች ማለት በሚነበብላቸው ቁርኣን የሚጠቀሙት መሆናቸውን፤
5. ጥንቃቄ ከቀደር እንደማያድን፤
6. ከተወሰነ ቁጥር በላይ አትውለድ በማለት ቤተሰብን መመጠን ክልክል መሆኑን፤
7. አላህ ለባሮቹ ማመቻቸት የፈለገው ማመቻቸት እንደሚችል፤
8. የወንጀል ስህተት መጥፎ መሆኑን፤
9. ተስፋ ማድረግ ያለውን ክብር፤
10. የእናትነት ርህራሄና እዝነት ምን እንደሚመስል፤
11. አላህ ባሮቹን እንዴት እንደሚንከባከብ፤
12. ነብዩ ሙሳን የሌሎች ሴቶችን ጡት እንዳይጠቡ አድርጎ ከእናታቸው እንዲጠቡ የማድረጉን ጥበብ፤
13. የአላህ ቀጠሮና ቃል ኪዳን በትክክል ተፈፃሚ መሆኑን፤
14. አላህ ለሙሳ ከመልዕክተኝነት በፊት የሰጣቸው ጥበብና እውቀት፤
15. ችግረኛን መርዳት ተገቢ ስለመሆኑ፤
16. ስህተት ላይ የወደቀ ሰው ወዲያውኑ መቶበት ግድ መሆኑ፤
17. ውለታን ማመስገን ተገቢ ስለመሆኑ፤
18. የመጥፎ ጓደኛ መዘዝ አደገኛ ስለ መሆኑ፤
19. ውስጥ ለውስጥ ህዝብን የሚበጠብጡ ሰዎች ከድርጊታቸው እንዲታቀቡ መንገር ግዴታ ስለ መሆኑ፤
20. አይን አፋርነት ለሁሉም ተገቢ ሲሆን ለሴቶች በይበልጥ ተገቢ መሆኑን፤
21. ሙሳ ሴቶችን ለመርዳት ያሳዩት ግብረገብነት፤
22. ስለ ዱዓ ትልቅነት፤
23. ፊትን ከባዕድ ወንድ መሸፈን የቀደምት ሙስሊም ሴቶች ሱና መሆኑን፤
24. የሹዐይብ ቸርነትና የነበራቸው ግርማ ሞገስ፤
25. መመጣጠን ማለት በስራ ስለመሆኑ፤
26. በስነ. ምግባሩና በእምነቱ ለሚያምኑበት ወንድ ልጄን አግባልኝ ብሎ መጠየቁ የሚቻል መሆኑን፤
27. በየትኛውም ስምምነት ላይ አላህን ማስመስከር ተገቢ መሆኑን፤
28. የነብዩ ሙሳን ትልቅነትና ስራ ወዳድነት በግልፅ እንማራለን።

۞ فَلَمَّا قَضَىٰ مُوسَى ٱلۡأَجَلَ وَسَارَ بِأَهۡلِهِۦٓ ءَانَسَ مِن جَانِبِ ٱلطُّورِ نَارٗاۖ قَالَ لِأَهۡلِهِ ٱمۡكُثُوٓاْ
إِنِّيٓ ءَانَسۡتُ نَارٗا لَّعَلِّيٓ ءَاتِيكُم مِّنۡهَا بِخَبَرٍ أَوۡ جَذۡوَةٖ مِّنَ ٱلنَّارِ لَعَلَّكُمۡ تَصۡطَلُونَ ٢٩

**29.** ሙሳም ጊዜውን በጨረሰና ከቤተሰቦቹ ጋር በሄደ ጊዜ ከጡር ተራራ ጎን እሳትን አየ፤ ለቤተሰብም እዚህ ቆዩ። እኔ እሳትን አየሁ፤ ከእርሷ አጠገብ ወሬ ወይም ትሞቁ ዘንድ ከእሳት ትንታግን (ችቦን) አመጣላችኋለሁ አለ።

فَلَمَّآ أَتَىٰهَا نُودِيَ مِن شَٰطِيِٕ ٱلۡوَادِ ٱلۡأَيۡمَنِ فِي ٱلۡبُقۡعَةِ ٱلۡمُبَٰرَكَةِ مِنَ ٱلشَّجَرَةِ أَن يَٰمُوسَىٰٓ
إِنِّيٓ أَنَا ٱللَّهُ رَبُّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٣٠ وَأَنۡ أَلۡقِ عَصَاكَۚ فَلَمَّا رَءَاهَا تَهۡتَزُّ كَأَنَّهَا جَآنّٞ وَلَّىٰ مُدۡبِرٗا
وَلَمۡ يُعَقِّبۡۚ يَٰمُوسَىٰٓ أَقۡبِلۡ وَلَا تَخَفۡۖ إِنَّكَ مِنَ ٱلۡأٓمِنِينَ ٣١ ٱسۡلُكۡ يَدَكَ فِي جَيۡبِكَ تَخۡرُجۡ
بَيۡضَآءَ مِنۡ غَيۡرِ سُوٓءٖ وَٱضۡمُمۡ إِلَيۡكَ جَنَاحَكَ مِنَ ٱلرَّهۡبِۖ فَذَٰنِكَ بُرۡهَٰنَانِ مِن رَّبِّكَ إِلَىٰ
فِرۡعَوۡنَ وَمَلَإِيْهِۦٓۚ إِنَّهُمۡ كَانُواْ قَوۡمٗا فَٰسِقِينَ ٣٢ قَالَ رَبِّ إِنِّي قَتَلۡتُ مِنۡهُمۡ نَفۡسٗا فَأَخَافُ أَن
يَقۡتُلُونِ ٣٣ وَأَخِي هَٰرُونُ هُوَ أَفۡصَحُ مِنِّي لِسَانٗا فَأَرۡسِلۡهُ مَعِيَ رِدۡءٗا يُصَدِّقُنِيٓۖ إِنِّيٓ أَخَافُ
أَن يُكَذِّبُونِ ٣٤ قَالَ سَنَشُدُّ عَضُدَكَ بِأَخِيكَ وَنَجۡعَلُ لَكُمَا سُلۡطَٰنٗا فَلَا يَصِلُونَ إِلَيۡكُمَا
بِـَٔايَٰتِنَآۚ أَنتُمَا وَمَنِ ٱتَّبَعَكُمَا ٱلۡغَٰلِبُونَ ٣٥

**30-35.** ወደ እሷ በመጣም ጊዜ ከሸለቆው ቀኝ ዳርቻ ከዛፊቱ በኩል በተባረከችው ስፍራ ውስጥ ሙሳ ሆይ! እኔ የዓለማት ጌታ አላህ ማለት እኔ ነኝ በማለት ተጠራ። በትርህንም ጣል ተባለ። እንደ ትንሽ እባብ ስትስለከለክ ባያትም ጊዜ ወደ ኋላ ዞሮ ሸሸ፤ አልተመለሰምም፤ ሙሳ ሆይ፣ ተመለስ አትፍራም፤ አንተ ከጥብቆቹ ነህና ተባለም። እጅህን በአንገትጌህ ውስጥ አግባ። ያለ ነውር ነጭ ሆና ትወጣለችና፤ ክንፍህንም ከፍርሃት ለመዳን ወደ አንተ አጣብቅ፤ እነዚህም ከጌታህ የሆኑ ወደ ፈርዖንና ወደ መኳንቶች የሚደርሱ ሁለት አስረጅዎች ናቸው፤ እነርሱ አመጠኞች ህዝቦች ነበሩና። ሙሳ አለ ጌታዬ ሆይ! እኔ ከእነርሱ ነፍስን ገድያለሁ ስለዚህ እንዳይገሉኝ እፈራለሁ። ወንድሜንም ሃሩን እርሱ ምላሱ ከእኔ የተባ (የተሻለ) ነው፤ እውነተኛነቴንም የሚያረጋግጥልኝ ረዳት ሆኖ ከእኔ ጋር ላከው እኔ ሊያስተባብሉኝ እፈራለሁና። አላህም፡- ጡንቻህን በወንድምህ በእርግጥ እናበረታለን፤ ለሁለታችሁም ስልጣንን እናደርጋለን፤ ወደ እናንተም በመጥፎ አይደርሱም። በታምራቶቻችን ሂዱ፤ እናንተና የተከተላችሁ ሁሉ አሸናፊዎች ናችሁ አላቸው።

فَلَمَّا جَآءَهُم مُّوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَا بَيِّنَٰتٖ قَالُواْ مَا هَٰذَآ إِلَّا سِحۡرٞ مُّفۡتَرٗى وَمَا سَمِعۡنَا بِهَٰذَا فِيٓ
ءَابَآئِنَا ٱلۡأَوَّلِينَ ٣٦ وَقَالَ مُوسَىٰ رَبِّيٓ أَعۡلَمُ بِمَن جَآءَ بِٱلۡهُدَىٰ مِنۡ عِندِهِۦ وَمَن تَكُونُ
لَهُۥ عَٰقِبَةُ ٱلدَّارِۚ إِنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٣٧ وَقَالَ فِرۡعَوۡنُ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمَلَأُ مَا عَلِمۡتُ لَكُم
مِّنۡ إِلَٰهٍ غَيۡرِي فَأَوۡقِدۡ لِي يَٰهَٰمَٰنُ عَلَى ٱلطِّينِ فَٱجۡعَل لِّي صَرۡحٗا لَّعَلِّيٓ أَطَّلِعُ إِلَىٰٓ إِلَٰهِ مُوسَىٰ
وَإِنِّي لَأَظُنُّهُۥ مِنَ ٱلۡكَٰذِبِينَ ٣٨ وَٱسۡتَكۡبَرَ هُوَ وَجُنُودُهُۥ فِي ٱلۡأَرۡضِ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّ وَظَنُّوٓاْ أَنَّهُمۡ
إِلَيۡنَا لَا يُرۡجَعُونَ ٣٩

**36-39.** ሙሳ በታዐምራቶቻችንን ግልጽ ሆነው ባመጣባቸው ጊዜ ይህ የተቀጠፈ ድግምት እንጅ ሌላ አይደለም፤ ይህንንም በመጀመሪያዎች አባቶቻችን ውስጥ አልሰማንም አሉ። ሙሳም ጌታዬ ከእርሱ ዘንድ በቀጥታው መንገድ የመጣውን ምስጉኒትም አገር ለእርሱ የምትሆንለትን ሰው ዐዋቂ ነው፤ እነሆ በደለኞች አይድኑም አለ። ፈርዖንም እናንተ ጭፍሮች ሆይ! ከእኔ ሌላ ለእናንተ አምላክን ምንም አላውቅም። ሃማን ሆይ፣ ጭቃን ለእኔ አቃጥልልኝ፤ ጡብ ስራልኝ ለእኔም ከፍተኛ ህንጻን ስራልኝ፤ ወደ ሙሳ አምላክ ልወጣ እከጅላለሁና፤ እኔም ከውሸታሞች መሆኑን እጠረጥረዋለሁ አለ። እርሱም ሰራዊቶቹም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ፤ እነርሱም ወደእኛ የማይመለሱ መሆናቸውን ጠረጠሩ።

فَأَخَذۡنَٰهُ وَجُنُودَهُۥ فَنَبَذۡنَٰهُمۡ فِي ٱلۡيَمِّۖ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلظَّٰلِمِينَ ٤٠
وَجَعَلۡنَٰهُمۡ أَئِمَّةٗ يَدۡعُونَ إِلَى ٱلنَّارِۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ لَا يُنصَرُونَ ٤١
وَأَتۡبَعۡنَٰهُمۡ فِي هَٰذِهِ ٱلدُّنۡيَا لَعۡنَةٗۖ وَيَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ هُم مِّنَ ٱلۡمَقۡبُوحِينَ ٤٢

**40-42.** እርሱንም ሰራዊቱንም በጥብቅ ያዝናቸው በባህርም ውስጥ ጣልናቸው የበደለኞች መጨረሻም እንዴት እንደነበረ ተመልከት። ወደ እሳት የሚጠሩ መሪዎችም አደረግናቸው፤ በትንሳኤም ቀን አይረዱም። በዚችም በቅርቢቱ ዓለም ውስጥ እርግማንን አስከተልናቸው። በትንሳኤም ቀን እነርሱ ከሚባረሩት ናቸው።

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَى ٱلۡكِتَٰبَ مِنۢ بَعۡدِ مَآ أَهۡلَكۡنَا ٱلۡقُرُونَ ٱلۡأُولَىٰ بَصَآئِرَ لِلنَّاسِ وَهُدٗى
وَرَحۡمَةٗ لَّعَلَّهُمۡ يَتَذَكَّرُونَ ٤٣

**43.** የፊተኞቹን የክፍለ ዘመናት ህዝቦችም ከአጠፋን በኋላ ለሰዎች የልብ ብርሃን መሪም እዝነትም ሲሆን ይገሠፁ ዘንድ ለሙሳ መጽሐፉን በእርግጥ ሰጠነው።

**ከታሪኮች ምዕራፍ ከአንቀፅ (29-43) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ቂሳስ ቀደም ሲልም ይሰራበት የነበረ ህግ እንደሆነ፤
2. ትዕዛዝ የተሰጠው ሰው የሚከብደው ከሆነ ከትዕዛዝ ሰጪው አካል እርዳታን መፈለግ ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. የህዝብ መሪዎችን በትዕግስትና በጥበብ ማገገዝ ተገቢ ስለ መሆኑ
4. ፊርአውን የአላህ ባሪያ መሆኑን ያውቅ እንደነበር፤
5. ኩራትና ትዕቢት የፊርዖን ባህሪ እንደነበር፤
6. የግፈኞች መጨረሻና መደምደሚያ ውድቀት እንደሆነ፤

وَمَا كُنتَ بِجَانِبِ ٱلْغَرْبِيِّ إِذْ قَضَيْنَآ إِلَىٰ مُوسَى ٱلْأَمْرَ وَمَا كُنتَ مِنَ ٱلشَّٰهِدِينَ ﴿٤٤﴾
وَلَٰكِنَّآ أَنشَأْنَا قُرُونًا فَتَطَاوَلَ عَلَيْهِمُ ٱلْعُمُرُ ۚ وَمَا كُنتَ ثَاوِيًا فِىٓ أَهْلِ مَدْيَنَ
تَتْلُواْ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتِنَا وَلَٰكِنَّا كُنَّا مُرْسِلِينَ ﴿٤٥﴾

**44-45.** ወደ ሙሳም ትዕዛዝን ባወረድንለት ጊዜ ከተራራው በምዕራባዊው ጎን አልነበርክም፤ ከተጣዱትም አልነበርክም። እኛ ግን ከእርሱ ኋላ አያሌ የክፍለ ዘመናትን ሰዎች አስገኘን። በእነርሱም ላይ ዕድሜዎች ተራዘሙ። በመድየንም ሰዎች ውስጥ ተቀማጭና በእነርሱ ላይ አንቀፆቻችንን የምታነብ አልነበርክም። እኛ ግን ላኪዎችህ በመሆናችን ነው።

وَمَا كُنتَ بِجَانِبِ ٱلطُّورِ إِذْ نَادَيْنَا وَلَٰكِن رَّحْمَةً مِّن رَّبِّكَ لِتُنذِرَ قَوْمًا مَّآ أَتَىٰهُم مِّن نَّذِيرٍ
مِّن قَبْلِكَ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ ﴿٤٦﴾ وَلَوْلَآ أَن تُصِيبَهُم مُّصِيبَةٌۢ بِمَا قَدَّمَتْ أَيْدِيهِمْ فَيَقُولُواْ
رَبَّنَا لَوْلَآ أَرْسَلْتَ إِلَيْنَا رَسُولًا فَنَتَّبِعَ ءَايَٰتِكَ وَنَكُونَ مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٤٧﴾ فَلَمَّا جَآءَهُمُ
ٱلْحَقُّ مِنْ عِندِنَا قَالُواْ لَوْلَآ أُوتِىَ مِثْلَ مَآ أُوتِىَ مُوسَىٰٓ ۚ أَوَلَمْ يَكْفُرُواْ بِمَآ أُوتِىَ مُوسَىٰ مِن
قَبْلُ ۖ قَالُواْ سِحْرَانِ تَظَٰهَرَا وَقَالُوٓاْ إِنَّا بِكُلٍّ كَٰفِرُونَ ﴿٤٨﴾

**46-48.** በጠራነውም ጊዜ በጡሩ ጎን አልነበርክም ግን ከአንተ በፊት ምንም አስፈራሪ ያልመጣቸውን ህዝቦች ታስፈራራ ዘንድ ከጌታህ በሆነ ችሮታ ላክንህ ሊገሠፁ ይከጀላልና። እጆቻቸውም ባሳለፉት ምክንያት መከራ የምትነካቸውና ጌታችን ሆይ! አንቀፆችህን እንድንከተል ከምእመናንም እንድንሆን ወደ እኛ መልዕክተኛን አትልክም ኖሯልን? (ይህ ሁሉ) የሚሉ ባልሆኑ ኖሮ አንልክም

ነበር። እውነቱም ከኛ ዘንድ በመጣላቸው ጊዜ ለሙሳ የተሰጠው ብጤ አይሰጠውም ኖሯልን? አሉ፤ ከዚህ በፊት ሙሳ በተሰጠው አልካዱምን? የተረዳዱ ሁለት ድግምቶች ናቸው አሉ፤ እኛ በሁሉም ከሓዲዎች ነንም አሉ።

قُلْ فَأْتُواْ بِكِتَٰبٍ مِّنْ عِندِ ٱللَّهِ هُوَ أَهْدَىٰ مِنْهُمَآ أَتَّبِعْهُ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٤٩﴾
فَإِن لَّمْ يَسْتَجِيبُواْ لَكَ فَٱعْلَمْ أَنَّمَا يَتَّبِعُونَ أَهْوَآءَهُمْۚ وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّنِ ٱتَّبَعَ هَوَىٰهُ
بِغَيْرِ هُدًى مِّنَ ٱللَّهِۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٥٠﴾

**49-50.** ከአላህ ዘንድ የሆነን መጽሐፍ እርሱ ከሁለቱም ይበልጥ ቅን የሆነን አምጡ፤ እውነተኞች እንደ ሆናችሁ ብታመጡት እከተለዋለሁ በላቸው። እሺ ባይሉህም የሚከተሉት ዝንባሌዎቻቸውን ብቻ መሆኑን ዕወቅ፤ ከአላህም የሆነ መምሪያ ሳይኖረው ዝንባሌውን የተከተለ ሰው ይበልጥ የጠመመ አንድም የለም፤ አላህ በደለኞች ህዝቦችን አይመራምና።

۞وَلَقَدْ وَصَّلْنَا لَهُمُ ٱلْقَوْلَ لَعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ ﴿٥١﴾ ٱلَّذِينَ ءَاتَيْنَٰهُمُ ٱلْكِتَٰبَ مِن قَبْلِهِۦ هُم
بِهِۦ يُؤْمِنُونَ ﴿٥٢﴾ وَإِذَا يُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ قَالُوٓاْ ءَامَنَّا بِهِۦٓ إِنَّهُ ٱلْحَقُّ مِن رَّبِّنَآ إِنَّا كُنَّا مِن قَبْلِهِۦ
مُسْلِمِينَ ﴿٥٣﴾ أُوْلَٰٓئِكَ يُؤْتَوْنَ أَجْرَهُم مَّرَّتَيْنِ بِمَا صَبَرُواْ وَيَدْرَءُونَ بِٱلْحَسَنَةِ ٱلسَّيِّئَةَ
وَمِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿٥٤﴾ وَإِذَا سَمِعُواْ ٱللَّغْوَ أَعْرَضُواْ عَنْهُ وَقَالُواْ لَنَآ أَعْمَٰلُنَا وَلَكُمْ
أَعْمَٰلُكُمْ سَلَٰمٌ عَلَيْكُمْ لَا نَبْتَغِى ٱلْجَٰهِلِينَ ﴿٥٥﴾

**51-55.** ይገሠፁም ዘንድ ቃልን ቁርኣንን በየአይነት ለእነርሱ በእርግጥ አስከታተልን። እነዚያ ከእርሱ በፊት መጽሐፍን የሰጠናቸው እነርሱ በእርሱ ያምናሉ። በእነርሱ ላይ በሚነበብላቸውም ጊዜ በእርሱ አምነናል፤ እርሱ ከጌታችን የሆነ እውነት ነው እኛ ከእርሱ በፊት ሙስሊሞች ነበርን ይላሉ። እነዚያ በመታገሳቸው ዋጋቸውን ሁለት* ጊዜ ይሰጣሉ፤ ክፉውንም ነገር በበጎ ምግባር ይገፈትራሉ፤ ከሰጠናቸውም ሲሳይ ይለግሳሉ። ውድቅንም ቃል በሰሙ ጊዜ ከእርሱ ይርቃሉ፤ ለእኛ ስራዎቻችን አሉን፤ ለእናንተም ስራዎቻችሁ አሉላችሁ። ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን ባለጌዎችን አንፈልግም ይላሉ።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ ማንኛውም ከመፅሐፍ ባለቤቶች መካከል ሆኖ ወደርሱ በተላከው ነብይ በእኔ ካመነ ሁለት ምንዳዎች አሉት።

ከታሪኮች (52) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦
ቀደም ሲል እውነትን ሲከተሉና ነብዩም ሲመጡ በትክክል ባመኑት የአይሁድ ምሁራን እንደእነረፋዓተል ቁርጡቢ ባሉት ሰሃቦች ምክንያት ነው።

إِنَّكَ لَا تَهۡدِي مَنۡ أَحۡبَبۡتَ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ يَهۡدِي مَن يَشَآءُۚ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُهۡتَدِينَ ﴿٥٦﴾

**56.** አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ አታቀናም፤ ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል እርሱም ቅኖዎችን* ዐዋቂ ነው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒድ እንዳስተላለፉት፤ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) «አቡ ጣሊብ ለሞት እየተቃረቡ ባለበትና አቡ ጀህል ከሳቸው ጋር እያለ ነብዩ ወደርሳቸው ገብተው «አጎቴ ሆይ! ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ጌታ የለም የምትለውንና አላህ ዘንድ የምከራከርበትን ቃል በል» አሉ። አቡ ጀህልና ዐብደላህ ኢብኑ አቡ ኡመይያህ በተደጋጋሚ «አቡ ጧሊብ ሆይ! የዐብዱል ሙጦሊብን ሃይማኖት ለመተው ትፈልጋለህን?» ይሏቸው ነበር። ከመሞታቸው በፊት ያሏቸው ነገር ቢኖር «በዐብዱል ሙጠሊብ ሃይማኖት ላይ ነኝ» የሚል ነበር። ነብዩም «ምንም የተከለከልኩ ቢሆንም ላንተ ምህረትን እጠይቅልሃለሁ» አሉ። በዚህም ሳቢያ «ለነብዩና ለነዚያ ላመኑት ለአጋሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች ቢሆኑም እንኳ እነሱ ከሓዲያን የእሳት ጓዶች መሆናቸው ከተገለፀላቸው በኋላ ምህረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም» አት. ተውባህ። «አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም፤ ግን አላህ...» (የታሪኮች ምዕራፍ 56) የሚለውን አንቀፅ አወረደ»

ከታሪኮች ምዕራፍ (56) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡጣሊብ በጠና ታምመው ሳለ አጠገባቸው አቡጀህልና ኡመያህ ነበረ። ነብዩ (ﷺ) ገብተው «አጐቴ ሆይ እባክህ ላኢላሀ ኢለሏህ በል። አላህ ዘንድ እንድመሰክርልህ»ሲሏቸው እነአቡ ጀህል «የአባትህን እምነት ልትተው ነው»በማለት ሲያስፈራሯቸው «እኔ በአባቴ እምነት ላይ ነኝ» በማለት ተስፋ የሚያስቆርጥ ንግግር ተናገሩ። ነብዩ በዚህ ሲያዝኑ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ዋሒዲ እና ሱዩጢ።

وَقَالُوٓاْ إِن نَّتَّبِعِ ٱلۡهُدَىٰ مَعَكَ نُتَخَطَّفۡ مِنۡ أَرۡضِنَآۚ أَوَلَمۡ نُمَكِّن لَّهُمۡ حَرَمًا ءَامِنًا يُجۡبَىٰٓ
إِلَيۡهِ ثَمَرَٰتُ كُلِّ شَيۡءٖ رِّزۡقًا مِّن لَّدُنَّا وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٥٧﴾

**57.** ከአንተ ጋር ቅንን መንገድ ብንከተል ከምድራችን እንነጠቃለን አሉም፤ ከእኛ ዘንድ የተሰጠ ሲሳይ ሲሆን የነገሩ ሁሉ ፍሬዎች ወደ እርሱ የሚሄዱበትን ፀጥተኛ ክልል መካን ለእነርሱ አላስመቸናቸውምን? ግን አብዛኞቻቸው አያውቁም።

ከታሪኮች ምዕራፍ (57) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ሐሪስ ኢብኑ ዑማን የተባለ ዘመዳቸው«የምትለው ትክክል መሆኑን እናውቃለን። ነገር ግን ሁሉም ስለተቃወመህ አንተን ብንከተል ዓረብ የተባለ ይበጣጥስናል ብለን ፈርተን ነው» በማለቱ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَكَمۡ أَهۡلَكۡنَا مِن قَرۡيَةِۭ بَطِرَتۡ مَعِيشَتَهَاۖ فَتِلۡكَ مَسَٰكِنُهُمۡ لَمۡ تُسۡكَن مِّنۢ بَعۡدِهِمۡ
إِلَّا قَلِيلٗاۖ وَكُنَّا نَحۡنُ ٱلۡوَٰرِثِينَ ﴿٥٨﴾

**58.** ከከተማም ኑሮዋን ምቾትዋን የካደችን ከተማ ያጠፋናት ብዙ ናት፤ እነዚህም ከእነርሱ በኋላ ጥቂት ጊዜ እንጂ ያጠፋናቸው ሲሆን መኖሪያዎቻቸው ናቸው፤ እኛም ከእነርሱ ወራሾች ነበርን።

وَمَا كَانَ رَبُّكَ مُهْلِكَ ٱلْقُرَىٰ حَتَّىٰ يَبْعَثَ فِىٓ أُمِّهَا رَسُولًا يَتْلُوا۟ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتِنَا ۚ
وَمَا كُنَّا مُهْلِكِى ٱلْقُرَىٰٓ إِلَّا وَأَهْلُهَا ظَٰلِمُونَ ﴿٥٩﴾

59. ጌታህም ከተሞችን በዋናዋ ከተማ ውስጥ አንቀፆቻችንን በእነርሱ ላይ የሚያነብ መልዕክተኛን እስከሚልክ ድረስ አጥፊ አልነበረም፤ ከተሞችንም ባለቤቶችዋ በዳዮች ሆነው እንጂ አጥፊዎች አልነበርን።

وَمَآ أُوتِيتُم مِّن شَىْءٍ فَمَتَٰعُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا وَزِينَتُهَا ۚ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰٓ ۚ أَفَلَا تَعْقِلُونَ ﴿٦٠﴾

60. (ሰዎች ሆይ)፣ በማንኛውም ነገር የተሰጣችሁት፤ የቅርቢቱ ሂይወት ጥቅምና ጌጣ ጌጥ ነው፤ አላህ ዘንድ ያለውም ምንዳ በጣም በላጭና ዘውታሪ ነው። አታውቁምን?

أَفَمَن وَعَدْنَٰهُ وَعْدًا حَسَنًا فَهُوَ لَٰقِيهِ كَمَن مَّتَّعْنَٰهُ مَتَٰعَ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا
ثُمَّ هُوَ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ مِنَ ٱلْمُحْضَرِينَ ﴿٦١﴾

61. መልካምን ተስፋ ቃል የገባንለትና እርሱም አግኚው የሆነ ሰው የቅርቢቱን ህይወት ጥቅም እንዳስመቸነውና ከዚያ እርሱ በትንሳኤ ቀን ለእሳት ከሚቀረቡት እንደ ሆነው ሰው ነውን?

وَيَوْمَ يُنَادِيهِمْ فَيَقُولُ أَيْنَ شُرَكَآءِىَ ٱلَّذِينَ كُنتُمْ تَزْعُمُونَ ﴿٦٢﴾ قَالَ ٱلَّذِينَ حَقَّ عَلَيْهِمُ
ٱلْقَوْلُ رَبَّنَا هَٰٓؤُلَآءِ ٱلَّذِينَ أَغْوَيْنَآ أَغْوَيْنَٰهُمْ كَمَا غَوَيْنَا ۖ تَبَرَّأْنَآ إِلَيْكَ ۖ مَا كَانُوٓا۟ إِيَّانَا
يَعْبُدُونَ ﴿٦٣﴾ وَقِيلَ ٱدْعُوا۟ شُرَكَآءَكُمْ فَدَعَوْهُمْ فَلَمْ يَسْتَجِيبُوا۟ لَهُمْ وَرَأَوُا۟ ٱلْعَذَابَ ۚ
لَوْ أَنَّهُمْ كَانُوا۟ يَهْتَدُونَ ﴿٦٤﴾

62-64. (አላህ) የሚጠራባቸውንና እነዚያ ተጋሪዎቼ ትሏቸው የነበራችሁት የት ናቸው? የሚልበትን ቀን (አስታውስ)። እነዚያ በእነርሱ ላይ ቅጣቱ የተረጋገጠባቸው ይላሉ ጌታችን ሆይ እነዚህ እነዚያ ያጠመምናቸው ናቸው፤ እንደጠመምን አጠመምናቸው (ከነሱ) ወደ አንተ ተጥራራን እኛን ይገዙ አልነበሩም። ለአላህ የምታጋሯቸውንም ጥሩ ይባላሉ፤ ይጠሩዋቸዋልም ግን ለእነርሱ አይመልሱላቸውም፤ ቅጣትንም ያያሉ እነርሱ ይመሩ በነበሩ ኖሮ (አያዩትም ነበር)።

وَيَوۡمَ يُنَادِيهِمۡ فَيَقُولُ مَاذَآ أَجَبۡتُمُ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ٦٥ فَعَمِيَتۡ عَلَيۡهِمُ ٱلۡأَنۢبَآءُ يَوۡمَئِذٖ فَهُمۡ
لَا يَتَسَآءَلُونَ ٦٦ فَأَمَّا مَن تَابَ وَءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحٗا فَعَسَىٰٓ أَن يَكُونَ مِنَ ٱلۡمُفۡلِحِينَ ٦٧

**65-67.** የሚጠራባቸውንና ለመልዕክተኞችም ምንን መለሳችሁ የሚልበትን ቀን አስታውስ። በዚያም ቀን ወሬዎች ሁሉ በእነርሱ ላይ ይሰወሩባቸዋል፤ እነርሱም አይጠያየቁም። የተፀፀተና ያመነ ሰውማ መልካምንም የሰራ ከሚድኑት ሊሆን ይከጀላል።

وَرَبُّكَ يَخۡلُقُ مَا يَشَآءُ وَيَخۡتَارُۗ مَا كَانَ لَهُمُ ٱلۡخِيَرَةُۚ سُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٦٨

**68.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህም የሚፈልገውን ይፈጥራል። ይመርጣልም። ለእነርሱ ለሰዎች ምርጫ የላቸውም። አላህ ከማይገባው ሁሉ ጠራ ከሚያጋሯቸውም ላቀ።

وَرَبُّكَ يَعۡلَمُ مَا تُكِنُّ صُدُورُهُمۡ وَمَا يُعۡلِنُونَ ٦٩

**69.** ጌታህም ለልቦቻቸው የሚደብቁትንና የሚገልፁትን ሁሉ ያውቃል።

وَهُوَ ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ لَهُ ٱلۡحَمۡدُ فِي ٱلۡأُولَىٰ وَٱلۡأٓخِرَةِۖ وَلَهُ ٱلۡحُكۡمُ وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ٧٠

**70.** እርሱም አላህ ነው፤ ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። ምስጋና በመጀመሪያይቱም በመጨረሻይቱም ዓለም ለእርሱ ብቻ ነው። ፍርዱም የእርሱ ብቻ ነው፤ ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ።

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِن جَعَلَ ٱللَّهُ عَلَيۡكُمُ ٱلَّيۡلَ سَرۡمَدًا إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ مَنۡ إِلَٰهٌ غَيۡرُ ٱللَّهِ
يَأۡتِيكُم بِضِيَآءٍۚ أَفَلَا تَسۡمَعُونَ ٧١

**71.** አያችሁን? (ንገሩኝ) አላህ በእናንተ ላይ ሌሊትን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ዘውታሪ ቢያደርገው ከአላህ ሌላ ብርሃንን የሚያመጣላችሁ አምላክ ማነው? አትሰሙምን? በላቸው።

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِن جَعَلَ ٱللَّهُ عَلَيۡكُمُ ٱلنَّهَارَ سَرۡمَدًا إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ مَنۡ إِلَٰهٌ غَيۡرُ ٱللَّهِ
يَأۡتِيكُم بِلَيۡلٖ تَسۡكُنُونَ فِيهِۚ أَفَلَا تُبۡصِرُونَ ٧٢ وَمِن رَّحۡمَتِهِۦ جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَ
لِتَسۡكُنُواْ فِيهِ وَلِتَبۡتَغُواْ مِن فَضۡلِهِۦ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ٧٣

**72-73.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አያችሁን? አላህ በእናንተ ላይ ቀንን እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስ ዘውታሪ ቢያደርገው ከአላህ ሌላ በውስጡ የምታርፉበትን ሌሊት የሚያመጣላችሁ አምላክ ማን ነው? እስቲ ንገሩኝ አታስተውሉምን? በላቸው፡፡ ከችሮታውም ለእናንተ ሌሊትንና ቀንን በውስጡ ልታርፉበት ከትሩፋቱም ልትፈልጉበት አመስጋኞችም ልትሆኑ አደረገላችሁ፡፡

وَيَوْمَ يُنَادِيهِمْ فَيَقُولُ أَيْنَ شُرَكَآءِىَ ٱلَّذِينَ كُنتُمْ تَزْعُمُونَ ﴿٧٤﴾ وَنَزَعْنَا مِن كُلِّ أُمَّةٍ شَهِيدًا فَقُلْنَا هَاتُوا۟ بُرْهَـٰنَكُمْ فَعَلِمُوٓا۟ أَنَّ ٱلْحَقَّ لِلَّهِ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَفْتَرُونَ ﴿٧٥﴾

**74-75.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሚጠራባቸውንም ቀንና እነዚያ ተጋሪዎቼ ትሉዋቸው የነበራችሁት የት ናቸው፡፡ የሚልበትን ቀን (አስታውስ)፡፡ ከህዝቦችም ሁሉ መስካሪን እናወጣለን፡፡ ያን ጊዜ እውነተኛውም አምላክነት ለአላህ ብቻ መሆኑን ያውቃሉ፡፡ ይቀጣጥፉት የነበሩትም ከእነርሱ ይጠፋባቸዋል፡፡

۞إِنَّ قَـٰرُونَ كَانَ مِن قَوْمِ مُوسَىٰ فَبَغَىٰ عَلَيْهِمْ ۖ وَءَاتَيْنَـٰهُ مِنَ ٱلْكُنُوزِ مَآ إِنَّ مَفَاتِحَهُۥ لَتَنُوٓأُ بِٱلْعُصْبَةِ أُو۟لِى ٱلْقُوَّةِ إِذْ قَالَ لَهُۥ قَوْمُهُۥ لَا تَفْرَحْ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلْفَرِحِينَ ﴿٧٦﴾ وَٱبْتَغِ فِيمَآ ءَاتَىٰكَ ٱللَّهُ ٱلدَّارَ ٱلْـَٔاخِرَةَ ۖ وَلَا تَنسَ نَصِيبَكَ مِنَ ٱلدُّنْيَا ۖ وَأَحْسِن كَمَآ أَحْسَنَ ٱللَّهُ إِلَيْكَ ۖ وَلَا تَبْغِ ٱلْفَسَادَ فِى ٱلْأَرْضِ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ ٱلْمُفْسِدِينَ ﴿٧٧﴾

**76-77.** ቃሩን ከሙሳ ነገዶች አንዱ ነበር፡፡ በእነርሱም ላይ አመፀ፡፡ ከድልቦችም ያንን መክፈቻዎቹ ብቻ የኃይል ባለቤቶች የሆኑ ጭፍሮችን ሸክሙ የሚከብድን ሰጠነው፡፡ ወገኖቹ ለእርሱ አትኩራ አላህ ኩራተኞችን አይወድምና ባሉት ጊዜ (አስታውስ)፡፡ አላህም በሰጠህ ሀብት የመጨረሻይቱን አገር ፈልግ፡፡ ሆኖም ከቅርቢቱ አለምም ፈንታህን አትርሳ፡፡ አላህ ወደ አንተ መልካምን እንዳደረገልህ ለሰዎች መልካምን አድርግ፡፡ በምድርም ውስጥ ማጥፋትን አትፈልግ፡፡ አላህ አጥፊዎችን አይወድምና አሉት፡፡

قَالَ إِنَّمَآ أُوتِيتُهُۥ عَلَىٰ عِلْمٍ عِندِىٓ ۚ أَوَلَمْ يَعْلَمْ أَنَّ ٱللَّهَ قَدْ أَهْلَكَ مِن قَبْلِهِۦ مِنَ ٱلْقُرُونِ مَنْ هُوَ أَشَدُّ مِنْهُ قُوَّةً وَأَكْثَرُ جَمْعًا ۚ وَلَا يُسْـَٔلُ عَن ذُنُوبِهِمُ ٱلْمُجْرِمُونَ ﴿٧٨﴾ فَخَرَجَ عَلَىٰ قَوْمِهِۦ فِى زِينَتِهِۦ ۖ قَالَ ٱلَّذِينَ يُرِيدُونَ ٱلْحَيَوٰةَ ٱلدُّنْيَا يَـٰلَيْتَ لَنَا مِثْلَ مَآ أُوتِىَ قَـٰرُونُ إِنَّهُۥ لَذُو حَظٍّ عَظِيمٍ ﴿٧٩﴾ وَقَالَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْعِلْمَ وَيْلَكُمْ ثَوَابُ ٱللَّهِ خَيْرٌ لِّمَنْ ءَامَنَ وَعَمِلَ صَـٰلِحًا ۚ وَلَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ٱلصَّـٰبِرُونَ ﴿٨٠﴾

**78-80.** (ሀብትን) የተሰጠሁት እኔ ዘንድ ባለው እውቀት ብቻ ነው አለ። አላህ ከእርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ሰዎች በኃይል ከእርሱ ይበልጥ የበረቱትን ሀብትን በመሰብሰብም ይበልጥ የበዙትን በእርግጥ ያጠፋ መሆኑን አያውቅምን? አመፀኞችም ከኃጢአቶቻቸው ምህረት የሚከተለውን ጥያቄ አይጠየቁም። በህዝቦቹም ላይ በጌጡ ውስጥ ሆኖ ወጣ፤ እነዚያ ቅርቢቱን ህይወት የሚፈልጉት ወይ ምኞታችን!፣ ቃሩን የተሰጠው ቢጤ ምነው ለእኛ በኖረን፤ እርሱ የታላቅ ዕድል ባለቤት ነውና አሉ። እነዚያም ዕውቀትን የተሰጡት ወዮላችሁ፣ የአላህ ምንዳ ለአመነ ሰው መልካምንም ለሰራ በላጭ ነው። ታጋሾችም እንጂ ሌላው አያገኛትም አሉ።

فَخَسَفۡنَا بِهِۦ وَبِدَارِهِ ٱلۡأَرۡضَ فَمَا كَانَ لَهُۥ مِن فِئَةٖ يَنصُرُونَهُۥ مِن دُونِ ٱللَّهِ
وَمَا كَانَ مِنَ ٱلۡمُنتَصِرِينَ ﴿٨١﴾ وَأَصۡبَحَ ٱلَّذِينَ تَمَنَّوۡاْ مَكَانَهُۥ بِٱلۡأَمۡسِ يَقُولُونَ وَيۡكَأَنَّ
ٱللَّهَ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦ وَيَقۡدِرُۖ لَوۡلَآ أَن مَّنَّ ٱللَّهُ عَلَيۡنَا لَخَسَفَ بِنَاۖ
وَيۡكَأَنَّهُۥ لَا يُفۡلِحُ ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴿٨٢﴾

**81-82.** በእርሱም በቤትም ምድርን ደረባን (አሰጠምን)። ለእርሱም ከአላህ ሌላ የሚረዱት ጭፍሮች ምንም አልነበሩትም። ከሚረዱትም አልነበረም። እነዚያም በትላንትናው ቀን ስፍራውን ይመኙ የነበሩት ወይ ጉድ! ለካ አላህ ከባሮቹ ለሚሻው ሰው ሲሳይን ያሰፋል። ያጠባልም። አላህ በእኛ ላይ በእምነት ባልለገሰልን ኖሮ ምድርን በእኛ ላይ በገለበጠብን ነበር፤ ወይ ጉድ! ከሓዲያን አይድኑም የሚሉ ሆነው አነጉ።

تِلۡكَ ٱلدَّارُ ٱلۡأٓخِرَةُ نَجۡعَلُهَا لِلَّذِينَ لَا يُرِيدُونَ عُلُوّٗا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَا فَسَادٗاۚ
وَٱلۡعَٰقِبَةُ لِلۡمُتَّقِينَ ﴿٨٣﴾ مَن جَآءَ بِٱلۡحَسَنَةِ فَلَهُۥ خَيۡرٞ مِّنۡهَاۖ وَمَن جَآءَ بِٱلسَّيِّئَةِ
فَلَا يُجۡزَى ٱلَّذِينَ عَمِلُواْ ٱلسَّيِّـَٔاتِ إِلَّا مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿٨٤﴾

**83-84.** ይህች የመጨረሻይቱ አገር ናት። ለእነዚያ በምድር ውስጥ ኩራትንና ማመፅን ለማይፈልጉት ሁሉ እናደርጋታለን። ምስጉኒቱም መጨረሻ ለጥንቁቆች ናት። በደግ ስራ የመጣ ሰው ለእርሱ ከእርሷ በላጭ ምንዳ አለው። በክፉም ስራ የመጡ ሰዎች እነዚያ መጥፎዎችን የሰሩ ይሰሩት የነበሩትን እንጂ አይመነዱም።

إِنَّ ٱلَّذِى فَرَضَ عَلَيْكَ ٱلْقُرْءَانَ لَرَآدُّكَ إِلَىٰ مَعَادٍۚ قُل رَّبِّىٓ أَعْلَمُ مَن جَآءَ بِٱلْهُدَىٰ وَمَنْ
هُوَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٨٥﴾ وَمَا كُنتَ تَرْجُوٓاْ أَن يُلْقَىٰٓ إِلَيْكَ ٱلْكِتَٰبُ إِلَّا رَحْمَةً مِّن رَّبِّكَۖ فَلَا
تَكُونَنَّ ظَهِيرًا لِّلْكَٰفِرِينَ ﴿٨٦﴾ وَلَا يَصُدُّنَّكَ عَنْ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ بَعْدَ إِذْ أُنزِلَتْ إِلَيْكَۖ وَٱدْعُ
إِلَىٰ رَبِّكَۖ وَلَا تَكُونَنَّ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿٨٧﴾ وَلَا تَدْعُ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَۘ
لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ كُلُّ شَىْءٍ هَالِكٌ إِلَّا وَجْهَهُۥۚ لَهُ ٱلْحُكْمُ وَإِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿٨٨﴾

**85-88.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያ፤ ቁርኣንን የተከፋፈለ ሆኖ በአንተ ላይ ያወረደው አምላክ ወደ መመለሻ ወደ መካ በእርግጥ መላሽህ ነው። ጌታዬ በቅን መንገድ የመጣውን ሰውና እርሱም በግልፅ ስህተት ውስጥ የሆነውን ሰው ዐዋቂ ነው በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መጽሐፉ ወደ አንተ መወረዱን ተስፋ የምታደርግ አልነበርክም፤ ግን ከጌታህ ችሮታ ተወረደልህ። ለከሓዲያን በፍፁም ረዳት አትሁን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአላህም አንቀፆች ወደ አንተ ከተወረዱ ጊዜ በኋላ አያግዱህ። ወደ ጌታህም ሰዎችን ጥራ። ከአጋሪዎችም አትሁን። ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ አትገዛ ከእርሱ በቀር አምላክ የለም ነገሩ ሁሉ ከአላህ በስተቀር ሁሉም ጠፊ ነው። ፍርዱ የእርሱ ብቻ ነው። ሁላችሁም ወደ እርሱ ትመለሳላችሁ።

**ከታሪኮች ምዕራፍ ከአንቀፅ (76-88) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሽፍትነትን በዱንያም በአኼራም እንደዚሁ እንደሚያስቀጣ፤
2. የሃይማኖት ትምህርት ያላቸው ሰዎች ሁልጊዜም ፍትሀዊ መሆናቸው፤
3. ጀነት የፈሪሃዊያን ስለ መሆን፤
4. እምነት ያለው ሰው ወደ ንሰሃ ለመግባት ቅርበት ያለው ስለመሆኑ፤
5. በሰዎች ላይ መኩራት ክልክል ስለመሆኑ፤
6. የአላህ ችሮታ ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ፤
7. የቁርኣን ትንበያ ተፈፃሚነቱ፤
8. ውይይት ሲደረግ አጠራጣሪ ሀሳቦችን በማቅረብ ነገሮችን ማለዘብ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
9. ከሓዲያን በተለይም በሙስሊሞች ላይ መርዳት ክልክል ስለ መሆኑ፤
10. በዳዕዋ ስራ ላይ ፅናትና ትዕግስት እንደሚያስፈልግ፤
11. ተውሒድን ሙቶ መነሳትን የነብዩን (ﷺ) ነብይት ማረጋገጥ፤
12. ከአላህ ሌላ ያሉ ነገሮች ሁሉ ትርፍ ስለ መሆናቸው፤
13. አላህ ፊት ያለው መሆኑንና ይህም ሲባል ማንንም ከመመሰል የፀዳ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የታሪኮች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (29)
# የሸረሪት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ዐንከቡት)

سُورَةُ العَنكَبُوتِ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (69) ናቸው።
### የሱረቱ አል ዓንከቡት መግቢያ

የወረደው ስልሳ ዘጠኝ አናቅፅን ይዞ ነው። የሰው ልጅ ሳይፈተን እንደማይቀርና የአባትና እናቱን ሀቅ እንዲጠብቅ አደራ ይላል። ሰዎች በእምነት እንደሚለያዩ ጠቁሞ ነብዩ ኑህ፤ ኢብራሂም፤ ሉጥ፤ ሹዐይብ፤ ሁድና ሳሊህ ከተላኩላቸው ሰዎች ጋር ያሳለፉትን ውጣ ውረድና መከራ እንዲሁም ከህዝቦቻቸው የገጠማቸውን የማስተባባል ሂደት በሰፊው ይተርካል። ጣኦትን ማምለክ ምንም አይነት ማስረጃ የሌለው ደካማ ለመሆኑ የማያሻማ ምሳሌውን በመስጠት አብራርቷል። በተጨማሪም ፈርዖን በሙሳ እንደከፈረ ሁሉ ከሓዲ የሆኑ ሰዎች ያልሆኑ ጥያቄዎችን እያቀረቡ እንደሚከፍሩ ይጠቁማል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓ ۝١ أَحَسِبَ ٱلنَّاسُ أَن يُتۡرَكُوٓاْ أَن يَقُولُوٓاْ ءَامَنَّا وَهُمۡ لَا يُفۡتَنُونَ ۝٢
وَلَقَدۡ فَتَنَّا ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۖ فَلَيَعۡلَمَنَّ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ صَدَقُواْ وَلَيَعۡلَمَنَّ ٱلۡكَٰذِبِينَ ۝٣
أَمۡ حَسِبَ ٱلَّذِينَ يَعۡمَلُونَ ٱلسَّيِّـَٔاتِ أَن يَسۡبِقُونَاۚ سَآءَ مَا يَحۡكُمُونَ ۝٤
مَن كَانَ يَرۡجُواْ لِقَآءَ ٱللَّهِ فَإِنَّ أَجَلَ ٱللَّهِ لَأٓتٖۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ۝٥

**1-5.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም (በእነዚህ ፊደሎች ምን እንደፈለገ አላህ ራሱ ብቻ ያውቃል)።* ሰዎች አምነናል በማለታቸው ብቻ (ከአላህ በልዩ ልዩ ነገሮች) ሳይፈተኑ የሚተው መሰላቸውን? እነዚያን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ህዝቦች በርግጥ ፈትነናል። እነዚያን እውነት የተናገሩትን አላህ በእርግጥ ያውቃል። ውሸታሞችንም ያውቃል። ወይንስ እነዚያ መጥፎዎችን ሥራዎች የሚሠሩት ሰዎች የሚያመልጡን መሰላቸውን? ያ የሚፈርዱት ፍርድ ከፋ። የአላህን መገናኘት ተስፋ የሚያደርግ ሰው ሁሉ ይዘጋጅ የአላህ ቀጠሮ በእርግጥ መጪ ነው። እርሱም (ንግግሮችን) ሰሚይም (ተግባሮችን) ዐዋቂ ነው።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፲ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَمَن جَٰهَدَ فَإِنَّمَا يُجَٰهِدُ لِنَفۡسِهِۦٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَغَنِيٌّ عَنِ ٱلۡعَٰلَمِينَ ۝٦ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ
ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَنُكَفِّرَنَّ عَنۡهُمۡ سَيِّـَٔاتِهِمۡ وَلَنَجۡزِيَنَّهُمۡ أَحۡسَنَ ٱلَّذِي كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ۝٧
وَوَصَّيۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ بِوَٰلِدَيۡهِ حُسۡنٗاۖ وَإِن جَٰهَدَاكَ لِتُشۡرِكَ بِي مَا لَيۡسَ لَكَ بِهِۦ عِلۡمٞ
فَلَا تُطِعۡهُمَآۚ إِلَيَّ مَرۡجِعُكُمۡ فَأُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ۝٨ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ
ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَنُدۡخِلَنَّهُمۡ فِي ٱلصَّٰلِحِينَ ۝٩

**6-9.** በአላህ መንገድ የታገለ ሰው የሚታገለው ለነፍሱ ነው። አላህ ከዓለማት ሁሉ በእርግጥ የተብቃቃ ነውና። እነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው ያመኑና መልካም ተግባራትን የሠሩ መጥፎ ሥራዎቻቸውን ከእነርሱ ላይ እናብስላቸዋለን። በዚያም ይሠሩት በነበሩት መልካም ሥራ በእርግጥ እንመነዳቸዋለን።* የሰውን ልጅ ለወላጆቹ መልካም ተግባርን ሁሉ እንዲፈፅም

አዘዝነው። ወላጆችም ለአንተም በእርሱ እውቀት የሌለህን ጣኦት በእኔ እንድታጋራው ቢያስገድዱህ አትታዘዛቸው። መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው። ከዚያም ትሠሩት የነበራችሁትን ሁሉ እነግራችኋለሁ። እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ሥራዎችን የሠሩ ሁሉ ከደጋጎቹ ውስጥ በእርግጥ እናስገባቸዋለን።

ከሸረሪት ምዕራፍ (8) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በሰዕድ ኢብኑ አቡወቃስ ምክንያት ነው። ሰዕድ ከእናቱ ተደብቆ ነበር የሰለመው። በሰማች ጊዜ «ሰዕድ ከአባትህ እምነት ወጣህ አሉ። ይህን የሙሐመድ እምነት እስካልተውክ ድረስ ወደጥላ አልጠለልም፤ አልበላም፤ አልጠጣም» አለቸው። ሰዕድ በእናቱ ዘንድ በጣም ተወዳጅ የነበረ ልጅ ነበር። ሆኖም በዚሁ ላይ እያሉ ሶስት ቀን አለፉ። ከዚያም በኋላ ሰዕድ ወደ ነብዩ መጥቶ ይህን ታሪክ ስለነገራቸው ይህ አንቀፅና በሉቅማንና በአህቃፍ ምዕራፎች ያሉት ተመሳሳይ አናቅፅ ወረዱ።

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَقُولُ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ فَإِذَآ أُوذِيَ فِي ٱللَّهِ جَعَلَ فِتۡنَةَ ٱلنَّاسِ كَعَذَابِ ٱللَّهِۖ
وَلَئِن جَآءَ نَصۡرٞ مِّن رَّبِّكَ لَيَقُولُنَّ إِنَّا كُنَّا مَعَكُمۡۚ أَوَلَيۡسَ ٱللَّهُ بِأَعۡلَمَ بِمَا فِي صُدُورِ
ٱلۡعَٰلَمِينَ ١٠ وَلَيَعۡلَمَنَّ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَلَيَعۡلَمَنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ ١١

**10-11.** ከሰዎች መካከል አመንን የሚል ሰው አለ። ከዚያ በአላህ በማመኑ ምክኒያት በተሰቃየ ጊዜ የሰዎችን ማሰቃየት እንደ አላህ ቅጣት ያደርጋል። ከጌታህም እርዳታ ቢመጣ እኛ በእርግጥ ከናንተ ጋር ነበርን ይላሉ። አላህ በዓለማት ሕዝብ ልቦች ውስጥ ያለውን ሁሉ ዐዋቂ አይደለምን? አላህ እነዚያን በትክክል ያመኑትን በእርግጥ ያውቃል። መናፍቆቹንም ያውቃል።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّبِعُواْ سَبِيلَنَا وَلۡنَحۡمِلۡ خَطَٰيَٰكُمۡ وَمَا هُم بِحَٰمِلِينَ
مِنۡ خَطَٰيَٰهُم مِّن شَيۡءٍۖ إِنَّهُمۡ لَكَٰذِبُونَ ١٢ وَلَيَحۡمِلُنَّ أَثۡقَالَهُمۡ وَأَثۡقَالٗا مَّعَ أَثۡقَالِهِمۡۖ
وَلَيُسۡـَٔلُنَّ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ عَمَّا كَانُواْ يَفۡتَرُونَ ١٣

**12-13.** እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ለእነዚያ ለአመኑት መንገዳችንን ተከተሉ። ኃጢአቶቻችሁንም እንሸከማለን አሉ። እነርሱም ከኃጢአቶቻቸው ምንንም ተሸካሚዎች አይደሉም። እነርሱ በእርግጥ ውሸታሞች ናቸው። ሸክሞቻቸውንና ከሸክሞቻቸው ጋር ሌሎች ሸክሞችንም በእርግጥ ይሸከማሉ። በትንሳኤም ቀን ይቀጥፏት ከነበሩት ሁሉ በእርግጥ ይጠየቃሉ።

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦ فَلَبِثَ فِيهِمۡ أَلۡفَ سَنَةٍ إِلَّا خَمۡسِينَ عَامٗا فَأَخَذَهُمُ ٱلطُّوفَانُ
وَهُمۡ ظَٰلِمُونَ ١٤ فَأَنجَيۡنَٰهُ وَأَصۡحَٰبَ ٱلسَّفِينَةِ وَجَعَلۡنَٰهَآ ءَايَةٗ لِّلۡعَٰلَمِينَ ١٥

**14-15.** ኑሕንም ወደ ህዝቦቹ በእርግጥ ላክነው። በውስጣቸውም ሺህ ዓመትን ሀምሳ ዓመት ሲቀር ተቀመጠ። እነርሱ በዳዮች ሆነውም የውሃው ማዕበል አጥለቀለቃቸው። ኑህንና የመርከቢቱን ጓዶች አዳንናቸው። እርሷንም ለዓለማት ተዐምር አደረግናት።

**ከሸረሪት ምዕራፍ አንቀፅ (1-15) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *ትክክለኛ እምነት ያለው ሁሉ መፈተኑ እንደማይቀር፤*
2. *አላህ ባሮቹን መፈተኑ የተለመደ መሆኑን፤*
3. *ወንጀለኞች ከአላህ ቁጥጥር የማያመልጡ መሆናቸውን፤*
4. *የሞት ቀጠሮ ቢረዝምም መጪ መሆኑን፤*
5. *በኸይር ስራ የሚለፋ ሰው ምንዳው ለራሱ መሆኑን፤*
6. *አላህ ከሰዎች ዒባዳ ምንም የማይፈልግ መሆኑን፤*
7. *እምነት በተግባር እንደሚገለፅ፤*
8. *አላህ ለሰዎች የሚከብዱ ነገሮችን ሊደነግግ የሚችል ሲሆን ከአቅም በላይ የሆነን ግን እንደማይደነግግ፤*
9. *የአላህ ቅጣት በመዘግየቷ የተታለሉ ሰዎችን ማስጠንቀቅ፤*
10. *የሙቶ መነሳትን ህቅነት ማረጋገጥ፤*
11. *ወላጆችን በመልካም ስራ ላይ መታዘዝ ግዴታ ስለመሆኑ፤*
12. *መልካም የሚሰሩ ሰዎች ከነብያትና ከእውነተኞች ጋር ጀነት እንደሚገቡ ማብሰር፤ እና መናፉቃን ማውገዝና አስመሳዮች በምላሳቸው አምነናል ብለው ቢያታልሉም አማኝ እንዳልሆኑ፤*
13. *አላህ ነብያትን ለምን እንደሚልክ፤*
14. *የነብዩ ኑህን ጥሪ የተከተሉ ሰዎች አናሳ ስለ መሆናቸው፤*
15. *አላህ ግፈኞችን አጥፍቶ አማኞችን ነፃ በማውጣት ማስተማሩን፤*

وَإِبۡرَٰهِيمَ إِذۡ قَالَ لِقَوۡمِهِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱتَّقُوهُۖ ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ١٦
إِنَّمَا تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوۡثَٰنٗا وَتَخۡلُقُونَ إِفۡكًاۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ تَعۡبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ
لَا يَمۡلِكُونَ لَكُمۡ رِزۡقٗا فَٱبۡتَغُواْ عِندَ ٱللَّهِ ٱلرِّزۡقَ وَٱعۡبُدُوهُ وَٱشۡكُرُواْ لَهُۥٓۖ إِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ١٧
وَإِن تُكَذِّبُواْ فَقَدۡ كَذَّبَ أُمَمٞ مِّن قَبۡلِكُمۡۖ وَمَا عَلَى ٱلرَّسُولِ إِلَّا ٱلۡبَلَٰغُ ٱلۡمُبِينُ ١٨
أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ كَيۡفَ يُبۡدِئُ ٱللَّهُ ٱلۡخَلۡقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥٓۚ إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ ١٩

**16-19.** መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ኢብራሒም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ የሆነውን (አስታውስ)። አላህን ተገዙ ፍሩትም ይህን ማድረጋችሁ የምታውቁት ብትሆኑ ለናንተ በላጭ ነው። (ሰዎች ሆይ!) ከአላህ ሌላ የምትገዙት ጣኦታትን ብቻ ነው። ውሸትንም ትቀጥፋላችሁ። እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣዖታት ለእናንተ ሲሳይን ሊሰጧችሁ አይችሉም። ስለዚህ ሲሳይን ከአላህ ዘንድ ብቻ ፈልጉ።

ተገዙትም ለርሱም አመስግኑ ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ። ብታስተባብሉም ከፊታችሁ የነበሩት ህዝቦች በእርግጥ አስተባብለዋል። በመልዕክተኛውም ላይ ግልፅ ማድረስ እንጂ ሌላ የለበትም። አላህ መፍጠርን እንዴት እንደሚጀምርና ከዚያ እንዴት እንደሚመልሰው አይመለከቱምን? ይህ በአላህ ላይ ቀላል ነው።

قُلْ سِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَٱنظُرُوا۟ كَيْفَ بَدَأَ ٱلْخَلْقَ ۚ ثُمَّ ٱللَّهُ يُنشِئُ ٱلنَّشْأَةَ ٱلْءَاخِرَةَ ۚ
إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٢٠﴾

**20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ላይ ሂዱ። እናም መፍጠርን እንዴት እንደጀመረ ተመልከቱ። ከዚያ አላህ የመጨረሻይቱን መነሳት ያስነሳል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና በላቸው።

يُعَذِّبُ مَن يَشَآءُ وَيَرْحَمُ مَن يَشَآءُ ۖ وَإِلَيْهِ تُقْلَبُونَ ﴿٢١﴾ وَمَآ أَنتُم بِمُعْجِزِينَ فِى ٱلْأَرْضِ
وَلَا فِى ٱلسَّمَآءِ ۖ وَمَا لَكُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ مِن وَلِىٍّ وَلَا نَصِيرٍ ﴿٢٢﴾ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِـَٔايَٰتِ
ٱللَّهِ وَلِقَآئِهِۦٓ أُو۟لَٰٓئِكَ يَئِسُوا۟ مِن رَّحْمَتِى وَأُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٢٣﴾

**21-23.** የሚሻውን ሰው ይቀጣል። የሚሻውንም ሰው ያዝንለታል ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ። (ሰዎች ሆይ!) እናንተ በምድርም ሆነ በሰማይ የምታቅቱ አይደላችሁም። ከአላህም ሌላ ወዳጅም ተከላካይም ምንም የላችሁም። እነዚያ በአላህ አንቀፆችና በመገናኘቱ የካዱ እነዚያ ከእዝነቴ ተስፋን ቆረጡ። እነዚያም ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

فَمَا كَانَ جَوَابَ قَوْمِهِۦٓ إِلَّآ أَن قَالُوا۟ ٱقْتُلُوهُ أَوْ حَرِّقُوهُ فَأَنجَىٰهُ ٱللَّهُ مِنَ ٱلنَّارِ ۚ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿٢٤﴾ وَقَالَ إِنَّمَا ٱتَّخَذْتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ أَوْثَٰنًا
مَّوَدَّةَ بَيْنِكُمْ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ ثُمَّ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ يَكْفُرُ بَعْضُكُم بِبَعْضٍ
وَيَلْعَنُ بَعْضُكُم بَعْضًا وَمَأْوَىٰكُمُ ٱلنَّارُ وَمَا لَكُم مِّن نَّٰصِرِينَ ﴿٢٥﴾

**24-25.** የህዝቦቹም መልስ፦ ግደሉት ወይም አቃጥሉት ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም። ከዚያም ከእሳቲቱ አላህ አዳነው። በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ሕዝቦች ብዙ ተዐምራቶች አሉበት። (ኢብራሂም) አለ፦ ከአላህ ሌላ ጣኦታትን አማልዕክት የያዛችሁት በቅርቢቱ ህይወት በመካከላችሁ ለመዋደድ ብቻ ነው። ከዚያ በትንሳኤ ቀን ከፊላችሁ በከፊሉ ይክዳል። ከፊላችሁም ከፊሉን ይረግማል። መኖሪያችሁም እሳት ናት። ለእናንተም ከረዳቶች ምንም የላችሁም።

۞ فَـَٔامَنَ لَهُۥ لُوطٌۘ وَقَالَ إِنِّي مُهَاجِرٌ إِلَىٰ رَبِّيٓۖ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٢٦

**26.** ሉጥም ለእርሱ አመነ። ኢብራሂምም እኔ ወደ ጌታዬ ተሰዳጅ ነኝ። እነሆ አላህ እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና አለ።

وَوَهَبۡنَا لَهُۥٓ إِسۡحَٰقَ وَيَعۡقُوبَ وَجَعَلۡنَا فِي ذُرِّيَّتِهِ ٱلنُّبُوَّةَ وَٱلۡكِتَٰبَ وَءَاتَيۡنَٰهُ أَجۡرَهُۥ فِي ٱلدُّنۡيَاۖ وَإِنَّهُۥ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ لَمِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ٢٧

**27.** ለእርሱም ኢስሐቅንና ያዕቆብን ሰጠነው በዘሩም ውስጥ ነብይነትንና መጽሐፍን አደረግን። ምንዳውንም በቅርቢቱ ዓለም ሰጠነው። እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከደጋጎቹ ነው።

وَلُوطًا إِذۡ قَالَ لِقَوۡمِهِۦٓ إِنَّكُمۡ لَتَأۡتُونَ ٱلۡفَٰحِشَةَ مَا سَبَقَكُم بِهَا مِنۡ أَحَدٖ مِّنَ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢٨ أَئِنَّكُمۡ لَتَأۡتُونَ ٱلرِّجَالَ وَتَقۡطَعُونَ ٱلسَّبِيلَ وَتَأۡتُونَ فِي نَادِيكُمُ ٱلۡمُنكَرَۖ فَمَا كَانَ جَوَابَ قَوۡمِهِۦٓ إِلَّآ أَن قَالُواْ ٱئۡتِنَا بِعَذَابِ ٱللَّهِ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ٢٩ قَالَ رَبِّ ٱنصُرۡنِي عَلَى ٱلۡقَوۡمِ ٱلۡمُفۡسِدِينَ ٣٠

**28-30.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሉጥንም ለሕዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ)። እናንተ ጠያፍን ሥራ ትሰራላችሁን? በእርሷ ከዓለማት አንድም አልቀደማችሁም። እናንተ በእርግጥ ወንዶችን ትመጣላችሁን? መንገድንም ትቆርጣላችሁን? በሸንጓችሁም የሚነወርን ነገር ትሠራላችሁን? አላቸው። የሕዝቦቹም መልስ ከእውነተኞቹ እነደሆንክ የአላህን ቅጣት አምጣብን ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም። ጌታዬ ሆይ! በአመፀኞች ሕዝቦች ላይ እርዳኝ አለ።

**ከሸረሪት ምዕራፍ ከአንቀፅ (16-30) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ዒባዳ ለአላህ ብቻ ስለመሆኑ፤
2. ከአላህ ሌላ ለማንም አምልኮ የተከለከለ ስለመሆኑ፤
3. ሰዎች ለጣኦት አምልኮ የተጋለጡት በድንቁርናና በድህነታቸው ምክንያት ስለ መሆኑ
4. አላህን ማመስገን ግዴታ ስለመሆኑ፤
5. ነብዩን (ﷺ) ማፅናናትና አጋሪዎችን ማውገዝ እና ዒባዳ ለአላህ ብቻ ስለመሆኑ፤
6. አዕምሮን ማሰራትና ለእምነት ማጠናከሪያ መጠቀም ተገቢ ስለመሆኑ፤
7. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
8. የሰው ልጅ ደካማ መሆኑንና ያለ አላህ መሸሻም ሆነ መጠጊያ እንደሌለው፤
9. የሚያስተባሉት ሰዎች በዚያው ባህሪያቸው ከሞቱ ጀነት እንደማይገቡ ማስጠንቀቅ፤

10. ግፈኞች በማስረጃ ሲያቅታቸው በጉልበት ወደ መጠቀም እንደሚያዘነብሉ፤
11. እሳት ኢብራሂምን አለማቃጠሉ አላህ በፈለገበት ጊዜ ምክንቶችን ሳይጠብቅ ሁኔታዎችን ማድረግ እንደሚያሳይ፤
12. የነብዩ ኢብራሂም የዳዕዋ ጥሪት ውጤት ደካማ እንደነበርና ያውም አንድ ሰው ሙስሊም እንደነበር፤
13. ለዲኑ ሲሉ ሀገራቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ለቀው የተሰደዱ ሰዎች በአላህ ዘንድ ያላቸው ክብር ከፍተኛ እንደሆነ፤
14. አላህ ለነብዩ ኢብራሂም የሰጣቸው ክብርና ማዕረግ ልዩ መሆኑን፤
15. ነብይነት ከኢብራሂም ቤተሰቦች እንደማይወጣ አላህ ቃል መግባቱን
16. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
17. ነብዩን (ﷺ) ማፅናናት፤
18. የግብረሰዶም ወንጀልን አስቀያሚነት፤
19. ግብረሰዶምን የፈፀሙ ሁሉ የዝሙት ህግ እንደሚፈፀምባቸው እንማራለን።

وَلَمَّا جَآءَتۡ رُسُلُنَآ إِبۡرَٰهِيمَ بِٱلۡبُشۡرَىٰ قَالُوٓاْ إِنَّا مُهۡلِكُوٓاْ أَهۡلِ هَٰذِهِ ٱلۡقَرۡيَةِۖ
إِنَّ أَهۡلَهَا كَانُواْ ظَٰلِمِينَ ٣١ قَالَ إِنَّ فِيهَا لُوطٗاۚ قَالُواْ نَحۡنُ أَعۡلَمُ بِمَن فِيهَاۖ
لَنُنَجِّيَنَّهُۥ وَأَهۡلَهُۥٓ إِلَّا ٱمۡرَأَتَهُۥ كَانَتۡ مِنَ ٱلۡغَٰبِرِينَ ٣٢

**31-32.** መልዕክተኞቻችንም ወደ ኢብራሂም በብስራት በመጡ ጊዜ እኛ የዚችን ከተማ ሰዎች አጥፊዎች ነን ሰዎችዋ በዳዮች ነበሩና አሉት። በእርሷ ውስጥ ሉጥ አለ እኮ አላቸው። እኛ በውስጧ ያለውን ከአንተ ይበልጥ ዐዋቂ ነን። እርሱን በእርግጥ እናድነዋለን። ቤተሰቦቹንም ጭምር ሚስቱ ብቻ ስትቀር እርሷ በጥፋቱ ውስጥ ከሚቀሩት ናት አሉት።

وَلَمَّآ أَن جَآءَتۡ رُسُلُنَا لُوطٗا سِيٓءَ بِهِمۡ وَضَاقَ بِهِمۡ ذَرۡعٗاۖ وَقَالُواْ لَا تَخَفۡ وَلَا تَحۡزَنۡ إِنَّا
مُنَجُّوكَ وَأَهۡلَكَ إِلَّا ٱمۡرَأَتَكَ كَانَتۡ مِنَ ٱلۡغَٰبِرِينَ ٣٣ إِنَّا مُنزِلُونَ عَلَىٰٓ أَهۡلِ هَٰذِهِ ٱلۡقَرۡيَةِ
رِجۡزٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ بِمَا كَانُواْ يَفۡسُقُونَ ٣٤ وَلَقَد تَّرَكۡنَا مِنۡهَآ ءَايَةَۢ بَيِّنَةٗ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ٣٥

**33-35.** መልዕክተኞቻችንም ወደ ሉጥ በመጡት ጊዜ በነሱ ምክንያት አዘነ። በእነርሱም ልቡ ተጨነቀ። አትፍራ አትዘንም። እኛ አዳኞችህ ነን። ቤተሰቦችህንም ሚስትህ ብቻ ስትቀር። እርሷ በጥፋቱ ውስጥ ከቀሪዎቹ ናት አሉትም። እኛ በዚህ ከተማ ሰዎች ላይ ያመጹ በነበሩበት ምክንያት ከሰማይ ቅጣትን አውራጆች ነን። በእርግጥም ለሚያስቡ ሰዎች ከእርሷ ግልጽ ምልክትን ተውን (አስቀረን)።

وَإِلَىٰ مَدۡيَنَ أَخَاهُمۡ شُعَيۡبٗا فَقَالَ يَٰقَوۡمِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱرۡجُواْ ٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَ وَلَا تَعۡثَوۡاْ فِي
ٱلۡأَرۡضِ مُفۡسِدِينَ ٣٦ فَكَذَّبُوهُ فَأَخَذَتۡهُمُ ٱلرَّجۡفَةُ فَأَصۡبَحُواْ فِي دَارِهِمۡ جَٰثِمِينَ ٣٧

**36-37.** ወደ መድየንም ወንድማቸውን ሹዐይብን ላክን። ህዝቦቼ ሆይ አላህን ተገዙ። የመጨረሻውንም ቀን ፍሩ። በምድርም ውስጥ የምታጠፉ ሆናችሁ አታበላሹ አላቸው። እናም አስተባበሉትና የምድር መንቀጥቀጥ ያዛቸው። ባገራቸውም ውስጥ ተንከፍረው አደሩ።

وَعَادٗا وَثَمُودَاْ وَقَد تَّبَيَّنَ لَكُم مِّن مَّسَٰكِنِهِمۡۖ وَزَيَّنَ لَهُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ أَعۡمَٰلَهُمۡ
فَصَدَّهُمۡ عَنِ ٱلسَّبِيلِ وَكَانُواْ مُسۡتَبۡصِرِينَ ٣٨

**38.** ዓድንና ሠሙድንም አጠፋን። የመኖሪያዎቻቸውን ፍርስራሾች በማየት መጥፋታቸው ለእናንተ በእውነት ተገለጠላችሁ። ሰይጣንም ሥራዎቻቸውን ለእነርሱ ሸለመላቸው። ከመንገድም አገዳቸው። የማስተዋልም ባለቤቶች ነበሩ። (ግን አላስተዋሉም)።

وَقَٰرُونَ وَفِرۡعَوۡنَ وَهَٰمَٰنَۖ وَلَقَدۡ جَآءَهُم مُّوسَىٰ بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَٱسۡتَكۡبَرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ
وَمَا كَانُواْ سَٰبِقِينَ ٣٩ فَكُلًّا أَخَذۡنَا بِذَنۢبِهِۦۖ فَمِنۡهُم مَّنۡ أَرۡسَلۡنَا عَلَيۡهِ حَاصِبٗا
وَمِنۡهُم مَّنۡ أَخَذَتۡهُ ٱلصَّيۡحَةُ وَمِنۡهُم مَّنۡ خَسَفۡنَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ وَمِنۡهُم مَّنۡ أَغۡرَقۡنَاۚ
وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيَظۡلِمَهُمۡ وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ يَظۡلِمُونَ ٤٠

**39-40.** ቃሩንንም ፈርዖንንም ሃማንንም አጠፋን። ሙሳም በተዐምራቶች በእርግጥ መጣባቸው። በምድርም ላይ ኮሩ። አምላጪዎች አልነበሩም። ሁሉንም በኃጢአቱ ያዝነው። ከእነርሱም ውስጥ ጠጠርን ያዘለ ነፍስን የላክንበት አለ። ከእነርሱም ውስጥ ጩኸት የያዘችው አለ። ከእነርሱም ውስጥ በእርሱ ምድርን የደረባንበት አለ። ከእነርሱም ውስጥ ያሰመጥነው አለ። አላህ የሚበድላቸው አልነበረም። ግን ነፍሶቻቸውን የሚበድሉ ነበሩ።

مَثَلُ ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوۡلِيَآءَ كَمَثَلِ ٱلۡعَنكَبُوتِ ٱتَّخَذَتۡ بَيۡتٗاۖ
وَإِنَّ أَوۡهَنَ ٱلۡبُيُوتِ لَبَيۡتُ ٱلۡعَنكَبُوتِۚ لَوۡ كَانُواْ يَعۡلَمُونَ ٤١
إِنَّ ٱللَّهَ يَعۡلَمُ مَا يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ مِن شَيۡءٖۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٤٢

**41-42.** የእነዚያ ከአላህ ሌላ ረዳቶችን (ጣኦታትን) የያዙ ሰዎች ምሳሌ ቤትን እንደሠራች ሸረሪት ብጤ ነው። ከቤቶችም ሁሉ በጣም ደካማው የሸረሪት ቤት ነው። ቢያውቁ ኖሮ አማልዕክት አድርገው አይገዟቸውም ነበር። አላህ ያንን ከእርሱ ሌላ የሚገዙትን ማንኛውንም ያውቃል። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

وَتِلۡكَ ٱلۡأَمۡثَٰلُ نَضۡرِبُهَا لِلنَّاسِۖ وَمَا يَعۡقِلُهَآ إِلَّا ٱلۡعَٰلِمُونَ ﴿٤٣﴾
خَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٤٤﴾

**43-44.** እነዚህንም ምሳሌዎች ለሰዎች እንገልጻቸዋለን። ከሊቃውንቶቹም በስተቀር ሌሎች አያውቋትም። አላህ ሰማያትንና ምድርን እውነተኛ ሆኖ ፈጠረ በዚህ ውስጥ ለምዕመናን ተዐምር አለበት።

ٱتۡلُ مَآ أُوحِيَ إِلَيۡكَ مِنَ ٱلۡكِتَٰبِ وَأَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَۖ إِنَّ ٱلصَّلَوٰةَ تَنۡهَىٰ عَنِ ٱلۡفَحۡشَآءِ وَٱلۡمُنكَرِۗ
وَلَذِكۡرُ ٱللَّهِ أَكۡبَرُۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ مَا تَصۡنَعُونَ ﴿٤٥﴾

**45.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመጽሐፉ ወደ አንተ የተወረደውን አንብብ። ሶላትንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ። ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና። አላህን ማውሳት ከመልካም ነገር ሁሉ በላጭ ነው። አላህም የምትሠሩትን ስራ ሁሉ ያውቃል።

۞ وَلَا تُجَٰدِلُوٓاْ أَهۡلَ ٱلۡكِتَٰبِ إِلَّا بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ إِلَّا ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ مِنۡهُمۡۖ وَقُولُوٓاْ ءَامَنَّا
بِٱلَّذِيٓ أُنزِلَ إِلَيۡنَا وَأُنزِلَ إِلَيۡكُمۡ وَإِلَٰهُنَا وَإِلَٰهُكُمۡ وَٰحِدٞ وَنَحۡنُ لَهُۥ مُسۡلِمُونَ ﴿٤٦﴾

**46.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) የመጽሐፉን ባለቤቶችን በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ክርክር እንጂ አትከራከሩ። ከእነርሱ እነዚያን የበደሉትን ሲቀር በሉም፡- በዚያ ወደ እኛ በተወረደው ወደ እናንተም በተወረደው አመንን። አምላካችንም አምላካችሁም አንድ ነው። እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን።

وَكَذَٰلِكَ أَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَۚ فَٱلَّذِينَ ءَاتَيۡنَٰهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ يُؤۡمِنُونَ بِهِۦۖ وَمِنۡ هَٰٓؤُلَآءِ مَن
يُؤۡمِنُ بِهِۦۚ وَمَا يَجۡحَدُ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَّا ٱلۡكَٰفِرُونَ ﴿٤٧﴾ وَمَا كُنتَ تَتۡلُواْ مِن قَبۡلِهِۦ مِن كِتَٰبٖ
وَلَا تَخُطُّهُۥ بِيَمِينِكَۖ إِذٗا لَّٱرۡتَابَ ٱلۡمُبۡطِلُونَ ﴿٤٨﴾ بَلۡ هُوَ ءَايَٰتُۢ بَيِّنَٰتٞ فِي صُدُورِ ٱلَّذِينَ
أُوتُواْ ٱلۡعِلۡمَۚ وَمَا يَجۡحَدُ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَّا ٱلظَّٰلِمُونَ ﴿٤٩﴾

**47-49.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እንደዚሁም ወደ አንተ መጽሐፍን አወረድን። እነዚያም መጽሐፍን የሰጠናቸው በእርሱ ያምናሉ። ከእነዚህም (ከመካ ሰዎች) በእርሱ የሚያምኑ አሉ። በተዐምራቶቻችንም ከሓዲያን እንጂ ማንም አይክድም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእርሱ በፊትም መጽሐፍን የምታነብ በቀኝህም የምትፅፈው አልነበርክም። ያን ጊዜ አጥፊዎች በእርግጥ በተጠራጠሩ ነበር። አይደለም እርሱ ቁርኣን በእነዚያ እውቀትን በተሰጡት ሰዎች ልቦች ውስጥ የጠለቀ ግልፆች አንቀፆች ነው። በአንቀፆቻችንም በዳዮቹ እንጂ ሌላው አይክድም።

وَقَالُواْ لَوْلَآ أُنزِلَ عَلَيْهِ ءَايَٰتٌ مِّن رَّبِّهِۦۖ قُلْ إِنَّمَا ٱلْـَٔايَٰتُ عِندَ ٱللَّهِ وَإِنَّمَآ أَنَا۠ نَذِيرٌ
مُّبِينٌ ﴿٥٠﴾ أَوَلَمْ يَكْفِهِمْ أَنَّآ أَنزَلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ يُتْلَىٰ عَلَيْهِمْۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَرَحْمَةً وَذِكْرَىٰ
لِقَوْمٍ يُؤْمِنُونَ ﴿٥١﴾ قُلْ كَفَىٰ بِٱللَّهِ بَيْنِى وَبَيْنَكُمْ شَهِيدًاۖ يَعْلَمُ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِۗ
وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِٱلْبَٰطِلِ وَكَفَرُواْ بِٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَٰسِرُونَ ﴿٥٢﴾

**50-52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲያን በእርሱ ላይ ከጌታው ዘንድ ተዐምራቶች ለምን አልተወረዱም አሉ። ተዐምራቶች አላህ ዘንድ ብቻ ናቸው። እኔም ግልጽ አስፈራሪ ብቻ ነኝ በላቸው። እኛ መጽሐፉን በእነርሱ ላይ የሚነበብ ኾኖ በአንተ ላይ ማውረዳችን አይበቃቸውምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ* ሕዝቦች ችሮታና ግሳጼ አለበት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእኔና በእናንተ መካከል መስካሪ በአላህ በቃ። በሰማያትና በምድር ያለውን ሁሉ ያውቃል በላቸው። እነዚያም በብላሽ ነገር ያመኑና በአላህ የካዱ እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎች ናቸው።

* በዚህ ጉዳይ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አላህ ለነብዩ (ﷺ) ባማረና በተዋበ ቅላጼ ቁርኣንን ያነቡት ዘንድ እንደፈቀደው አይነት ሌላ ነገርን አልፈቀደም።»

በቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ሁለት አይነት ሰዎችን ለመሆን ከመመኘት በስተቀር ሌላ አይነት ሰዎችን ለመሆን አልፈቅድም። እነርሱም፦ አንድ ሰው አላህ ቁርኣንን ካስተማረው በኋላ ይህን የተማረውን ሌትና ቀን እንደሚቀራ አይነት ሰው፤ ይህ ሰው ቁርኣንን በሚቀራበት ወቅት ከጎረቤቶቹ መካከል አንዱ እከሌ የተሰጠው አይነት ቢሰጠኝ የሚሰራው አይነት ስራ እሰራ ነበር» ይላል። ሌላው አላህ ሀብት ሰጥቶት ከዚም በኋላ እሱም ይህን ገንዘብ በትክክለኛው መንገድ ላይ የሚያውለው የሚሰጥ አይነት ሰውን ነው። ሌላው ሰውም «እከሌ የተሰጠውን አይነት ቢሰጠኝ ኖሮ፤ እሱ የሚሰራውን እሰራ ነበር ይላል»

وَيَسۡتَعۡجِلُونَكَ بِٱلۡعَذَابِ وَلَوۡلَآ أَجَلٞ مُّسَمّٗى لَّجَآءَهُمُ ٱلۡعَذَابُۚ وَلَيَأۡتِيَنَّهُم بَغۡتَةٗ وَهُمۡ
لَا يَشۡعُرُونَ ٥٣ يَسۡتَعۡجِلُونَكَ بِٱلۡعَذَابِ وَإِنَّ جَهَنَّمَ لَمُحِيطَةُۢ بِٱلۡكَٰفِرِينَ ٥٤ يَوۡمَ
يَغۡشَىٰهُمُ ٱلۡعَذَابُ مِن فَوۡقِهِمۡ وَمِن تَحۡتِ أَرۡجُلِهِمۡ وَيَقُولُ ذُوقُواْ مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ٥٥

**53-55.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በቅጣትም ያስቸኩሉሃል የተወሰነም ጊዜ ባልነበረ ኖሮ ቅጣቱ በመጣባቸው ነበር። እነርሱ የማያውቁ ሲኾኑም በድንገት በእርግጥ ይመጣባቸዋል። በቅጣት ያስቸኩሉሃል ገሀነምም በከሓዲዎች በእርግጥ ከባቢ ናት። ቅጣቱ ከበላያቸው ከእግሮቻቸውም ሥር በሚሸፍናቸው ቀን ትሰሩት የነበራችሁትን ቅመሱ በሚላቸውም (ቀን ትከባቸዋለች)።

يَٰعِبَادِيَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّ أَرۡضِي وَٰسِعَةٞ فَإِيَّٰيَ فَٱعۡبُدُونِ ٥٦ كُلُّ نَفۡسٖ ذَآئِقَةُ
ٱلۡمَوۡتِۖ ثُمَّ إِلَيۡنَا تُرۡجَعُونَ ٥٧ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَنُبَوِّئَنَّهُم
مِّنَ ٱلۡجَنَّةِ غُرَفٗا تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَاۚ نِعۡمَ أَجۡرُ ٱلۡعَٰمِلِينَ ٥٨
ٱلَّذِينَ صَبَرُواْ وَعَلَىٰ رَبِّهِمۡ يَتَوَكَّلُونَ ٥٩

**56-59.** እናንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ምድሬ በእርግጥ ሰፊ ናት። ብትቸገሩ ተሰደዱ እኔንም ብቻ ተገዙኝ።* ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት። ከዚያ ወደ እኛ ትመለሳላችሁ። እነዚያም ያመኑና መልካም ስራዎችን የሠሩ ከገነት በስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ሰገነቶች በውስጣቸው ዘውታሪዎች ሲኾኑ በእርግጥ እናሰፍራቸዋለን። የሠራተኞች ምንዳ ምንኛ አማረ! እነርሱ እነዚያ የታገሱ በጌታቸውም ላይ የሚመኩ ናቸው።

✴ የአላህ መልዕክተኛ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሙዓዝ እንዳስተላለፉት እኔ ከነብዩ ኋላ እየጋለብኩ ሳለሁ «ሙዓዝ ሆይ!» አሉኝ። እኔም «አቤት!» አልኳቸው። እሳቸውም ይህን መሰሉን አጠራር ሶስት ጊዜ ደጋግመውታል። ከዚያም «አላህ በባሪዎቹ ላይ ያላውን ሐቅ ታውቃለህን?» አሉኝ። እኔም አላህና መልዕክተኛው በበለጠ ያውቃሉ» አልኳቸው። እሳቸውም «የእሱ ሐቅ እሱን ብቻ እንዲያመልኩና ከእሱ ጋር ሌላ አምልኮትን እንዳይዙ ነው» አሉ። አሁንም «ሙዓዝ ሆይ!» ብለው ተጣሩ። እኔም «አቤት!» አልኳቸው«የአላህ ባሪያዎች በአላህ ላይ ያላቸው ሐቅስ ምን እንደሆነ ታውቃለህን?» ብለው አሉኝ። እኔም፤ «አላህና መልዕክተኛው በበለጠ ያውቃሉ» አልኳቸው። እሳቸውም «የአላህ ባሪያዎች በአላህ ላይ ያላቸው ሐቅ እነርሱ ያን ከተገበሩ እንዳይቀጣቸው ነው» አሉኝ።

وَكَأَيِّن مِّن دَآبَّةٍ لَّا تَحۡمِلُ رِزۡقَهَا ٱللَّهُ يَرۡزُقُهَا وَإِيَّاكُمۡۚ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ٦٠

**60.** ከተንቀሳቃሽ ፍጡራን ምግባቸውን ለመሸከም የማይችሉ ብዙ ናቸው። አላህ ይመግባቸዋል። እናንተንም ይመግባል። እርሱ ሰሚና ዐዋቂ ነውና።

وَلَئِن سَأَلۡتَهُم مَّنۡ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَسَخَّرَ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُۖ فَأَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ٦١ ٱللَّهُ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ مِنۡ عِبَادِهِۦ وَيَقۡدِرُ لَهُۥٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ ٦٢

**61-62.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ፀሐይንና ጨረቃንም የገራ ማን እንደኾነ ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው ይሉሃል። ታዲያ እንዴት ይመለሳሉ። አላህ ከባሮቹ ለሚሻው ሲሳይን ያሰፋል። ለእርሱም ያጠባል። አላህ በነገሩ ሁሉ አዋቂ ነውና።

وَلَئِن سَأَلۡتَهُم مَّن نَّزَّلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَأَحۡيَا بِهِ ٱلۡأَرۡضَ مِنۢ بَعۡدِ مَوۡتِهَا لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُۚ قُلِ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِۚ بَلۡ أَكۡثَرُهُمۡ لَا يَعۡقِلُونَ ٦٣ وَمَا هَٰذِهِ ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَآ إِلَّا لَهۡوٞ وَلَعِبٞۚ وَإِنَّ ٱلدَّارَ ٱلۡأٓخِرَةَ لَهِيَ ٱلۡحَيَوَانُۚ لَوۡ كَانُواْ يَعۡلَمُونَ ٦٤

**63-64.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሰማይ ውሃን ያወረደና በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ሕያው ያደረጋት ማን እንደኾነ ብትጠይቃቸው አላህ ነው ይሉሃል። ስለዚህ ምስጋና ሁሉ ለአላህ ነው በላቸው። ግን አብዛኞቻቸው ይህን አያውቁም። ይህም የቅርቢቱ ሕይወት መታለያና ጨዋታ እንጂ ሌላ አይደለም። የመጨረሻይቱም አገር እርሷ በእርግጥ የዘላለም ህይወት አገር ናት። የሚያውቁ* ቢኾኑ ኖሮ ጠፊይቱን ሕይወት አይመርጡም ነበር።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በመጀመሪያ ወደ ጀነት የሚገቡ ሰዎች ልክ እንደ ሙሉ ጨረቃ ብርሃን ይደምቃሉ። በውስጧም አይጠፉም፤ አይናወጡም፤ አይፀዳዱም። እቃቸው በሙሉ ከወርቅ የተሰራ ነው። እንዲሁም ማበጠሪያዎቻቸው ከወርቅና ከብር የተሰሩ ናቸው። ጠረናቸው ልክ እንድ ሚስክ መልካም መአዛ አለው። እያንዳንዳቸው ሁለት ሚስቶች አሏቸው። እጅግ ቆንጆ ከመሆናቸው የተነሳ የአጥንቶቻቸው መቅኒ ይታያል። የጀነት ሰዎች በመካከላቸው ልዩነትና የጠላትነት ባህሪ የላቸውም። ልቦናዎቻቸው ልክ እንደ አንድ ልቦና ነው። አላህንም ቀንና ለሊት ያወድሳሉ።»

فَإِذَا رَكِبُوا۟ فِى ٱلْفُلْكِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ إِذَا هُمْ يُشْرِكُونَ ﴿٦٥﴾ لِيَكْفُرُوا۟ بِمَآ ءَاتَيْنَـٰهُمْ وَلِيَتَمَتَّعُوا۟ ۖ فَسَوْفَ يَعْلَمُونَ ﴿٦٦﴾

**65-66.** በመርከቦች ውስጥ በተሳፈሩ ጊዜም አላህን መገዛትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ኾነው ይጠሩታል። ወደ የብስ በማውጣት ባዳናቸው ጊዜ ግን ወዲያውኑ እነርሱ ጣዖትን ያጋራሉ። በሰጠናቸው ፀጋ ሊክዱና ሊጠቃቀሙ ያጋራሉ ወደ ፊትም የሚጠብቃቸውን ያውቃሉ።

أَوَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّا جَعَلْنَا حَرَمًا ءَامِنًا وَيُتَخَطَّفُ ٱلنَّاسُ مِنْ حَوْلِهِمْ ۚ أَفَبِٱلْبَـٰطِلِ يُؤْمِنُونَ وَبِنِعْمَةِ ٱللَّهِ يَكْفُرُونَ ﴿٦٧﴾ وَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّنِ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَوْ كَذَّبَ بِٱلْحَقِّ لَمَّا جَآءَهُۥٓ ۚ أَلَيْسَ فِى جَهَنَّمَ مَثْوًى لِّلْكَـٰفِرِينَ ﴿٦٨﴾

**67-68.** ሰዎቹ ከየዙሪያቸው ሲነጠቁ እኛ አገራቸውን ፀጥተኛ ክልል ማድረጋችንን አያዩምን? በውድቅ ነገር ያምናሉን? በአላህስ ፀጋ ይክዳሉን? በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ሰው ወይም እውነት በመጣለት ጊዜ ከአስዋሸ ሰው ይበልጥ ራሱን በዳይ ማነው? በገሀነም ውስጥ ለከሓዲያን መኖሪያ የለምን?

وَٱلَّذِينَ جَـٰهَدُوا۟ فِينَا لَنَهْدِيَنَّهُمْ سُبُلَنَا ۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَمَعَ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٦٩﴾

**69.** እነዚያም በእኛ መንገድ የታገሉ መንገዳችንን በእርግጥ እንመራቸዋለን። አላህ በእርግጥ ከበጎ ሰሪዎች ጋር ነው።

**ከሸረሪት ምዕራፍ ከአንቀፅ (31-69) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ተውሒድንና ነብይነትን፤ ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
2. በምድር ላይ ብክለትን ማውገዝ፤
3. በግፈኞች ላይ የአላህ ብቀላ ምን ያህል ያነጣጠረ መሆኑን፤
4. ሰይጣን ለሰዎች ጥፋት ዋና ምክንያት እንደሆነ፤
5. የኩራት መጨረሻ፤
6. ምሳሌዎችን መጥቀስ ለማስተማር አስፈላጊ መሆኑን፤
7. ተውሒድን ማፅደቅና ሽርክን ማውገዝ፤
8. ዐሊሞች ያላቸው ክብር ከፍተኛ መሆኑን፤
9. ቁርአንን መቅራት፤ ሶላትን መስገድ፤ ዚክር መዘከር ተገቢ ስለ መሆኑ፤
10. የመፅሐፍት ሰዎችን መከራከር ተገቢ ስለመሆኑ፤
11. የመፅሐፍ ሰዎችን መጠየቅ ክልክል ስለመሆኑ፤

12. የመፅሐፍ ባለቤቶች ባሉን ሁሉ ማመን እንደ ሌለብን፤
13. ከነብዩ (ﷺ) ባህሪያት አንዱ ኡሚይነት አለ መፃፍና አለ ማንበብ መሆኑን፤
14. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
15. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ለማረጋገጥ ዋናው ቁርአን ስለመሆኑ፤
16. ቁርአን ለሰዎች መገሰጫና መምከሪያ ስለ መሆኑ፤
17. እውነትን እምቢ ብለው ውሸትን ተሸክመው የሚጓዙ ከሓዲያን መክሰራቸውን ማሳወቅ፤
18. በሚያስገርም ነገር መገረም ተገቢ ስለ መሆኑ፤
19. የመካ ከሓዲያን የነበሩበትን ሞኝነትና ድንቁርና በግልፅ ማሳወቅ፤
20. አላህ ቅጣቶችን የሚያዘገየው አቅቶት ሳይሆን እሱ ብቻ ለሚያውቀው ምክንያት ስለ መሆኑ፤
21. የከሓዲያን እርስ በርስ መቃረንን፤
22. መከበርም ሆነ መደህየት የአላህን ውዴታም ሆነ ጥላቻን እንደማያሳይ፤
23. የዱንያን ዝቅተኝነትና የአኼራን ትልቅነት መግለፅን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የሸረሪት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (30)
# የሮም ምዕራፍ
## (ሱረቱ አርሩም)

سُورَةُ الرُّومِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (60) ናቸው።
### የሱረቱ አርሩም መግቢያ

የሮማውያንን ሽንፈት በማውሳትና ለሙዕሚኖች ሮሞችን በፋርሶች ላይ ድል እንደሚሰጣቸው ቃል በመግባት ነው የሚጀምረው። በአላህ ፍጡር በሆነው በምድር ላይ በመጓዝ መመራመር እንደሚያስፈልግ፤ ይህም ከቁርይሾች በበለጠ ምድርን አስውበዋት የነበሩትን ቀደምት ከሓዲያንን መጨረሻ እንዲያውቁ መሆኑንም ይጠቁማል።

የቂያማ ዕለት ሰዎች ምን አይነት ባህሪ እንደሚኖራቸው መጠቆም በሌሊትና በቀን አላህን የሚያጠሩትንና የሚያመልኩትን አማኞች ያወድሳል። የአላህን አንድነት ከሚያመለክቱ ነገሮች መካከል የሌሊትና የቀንን መቀያየር፤ የቋንቋዎችን ብዛት መሆናቸውን ያወሳል። የሽርክን ደካማ ጎን በማጋለጥ ሰዎች እንዲርቁት ግፊት አድርጓል።

አላህ ለቤተሰብና ለማህበረሰብ ትስስር የሚጠቅሙ ነገሮችን ይጠቁማል። ወለድንም በግልጽ ይከለክላል። ዘካንም ይደነግጋል። ለዘመድ መልካም መዋልን በጥብቅ ያዝዛል።

እንደዚህ የተባለችው ምድር የትኛዋ ሀገር እንደሆነችና ዝቅተኝነቷ ከምን አኳያ እንደሆነ የዘመኑ ቁርኣን እንዲህ ይላል። «አሊፍ ላም ሚይም) ሩም ተሸነፈች በጣም ቅርብ በሆነችው ምድር። እነርሱም ከመሸነፋቸው በኋላ በእርግጥ ያሸንፋሉ። በጥቂት ዓመታት ውስጥ (ያሸንፋሉ) ትዕዛዙ በፊትም በኋላም የአላህ ነው። በዚያ ቀንም ምዕመናን ይደሰታ። በአላህ እርዳታ (ይደሰታሉ) የሚሻውን ሰው» (የሮም ምዕራፍ፡ 1-6)

ፋርሶች (ጣኦታዊያን) በጦር ሰራዊትና በመሳሪያ ብቃታቸው ሮሞችን (ክርስቲያኖችን) በጦር መሳሪያቸው ማነስና በሰራዊታቸው ደካማነት የተነሳ ድል ነሷቸው። አሸንፏቸው። በመካ ይኖሩ የነበሩ መሰል ጣኦታዊያኖች (ቁረይሾች) በዚህ ድል በመደሰት በመካ ሙስሊሞች ላይ «ሮሞች እንደተዋረዱ እናንተም ትዋረዳላችሁ» በማለት ዛቱባቸው። መቼም ምንም ቢሆን ከጣኦታዊያኖች ይልቅ ክርስቲያኖች ለሙስሊሞች የቀረቡ ናቸው። ሶሀቦችም የሮሞቹ መሸነፍና የቁረይሾች ዛቻ ልባቸውን በሀዘን ሞላው። በዚህ ጊዜ አላህ «ሮሞች ቢሸነፉም በቅርብ ጊዜ ውስጥ ግን (ከዘጠኝ ዓመት ባልበለጠ) በአላህ እርዳታ ኃይልን አግኝተው ድልን ይጎናፀፋሉ። የዛኔም ሙስሊሞች ይደሰታሉ» በማለት ቁርአናዊ ትንቢትን አወረደ። ቁረይሾች «በፍፁም! በዚህ ጥቂት ዓመታት ውስጥ ሮሞች አያሸንፉም» በማለት ከሶሀባው አቡበክር ጋር ተወራረዱ። ጊዜውንም መጠባበቅ ጀመሩ ሰባት ዓመታት ያህል ሮሞች በአላህ እርዳታ ፋርሶችን ድል መቱ። የቁርኣንም ትንቢት ፍፃሜን አገኘ።

መጀመሪያ ላይ ያሉት (6) አናቅፅ በአጭሩ አራት ነገሮች አጠቃለዋል። እነሱም፡-

1. አላህ ቀጠሮውን እንደማያፈርስ፤
2. ብዙ ከሓዲያን እንደማያውቁ፤
3. ከሓዲያን በቅርቢቱ ህይወት ግልፁን ብቻ እንደሚያውቁ፤
4. ከሓዲያን በኋለኛይቱ ዓለም ዘንጊዎች ናቸው። አሁን አሁን ነጮች በቴክኖሎጂ ማደጋቸውና በዱንያዊ እውቀት መምጠቃቸውን እያዩ ለዚህ ያልታደሉትን የሙስሊም ማህበረሰብ ኋላቀር አድርገው የሚቆጥሩ አናቅፅ በርካቶች ናቸው። ነገሩ ግን ሙስሊሞች በቴክኖሎጂ ትምህርት መጠንከር ቢኖርባቸዉም የዲናቸውን ጉዳይ ጠንቅቀቀው ካወቁ ይህን ያህል ሊያስወግዛቸው አይገባም። በቴክኖሎጂ ትምህርት ሙስሊሙ መሳተፍ እንዳለበት ከሚያመለክቱ የቁርኣን አናቅፅ መካከል በሱረቱ አት-ተውበህ.

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓ ﴿١﴾

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም። (በእነዚህ ፊደሎች ምን እንደፈለገ አላህ ራሱ ብቻ ያውቃል)።*

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፤ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርአን ታአምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

غُلِبَتِ ٱلرُّومُ ﴿٢﴾ فِيٓ أَدۡنَى ٱلۡأَرۡضِ وَهُم مِّنۢ بَعۡدِ غَلَبِهِمۡ سَيَغۡلِبُونَ ﴿٣﴾
فِي بِضۡعِ سِنِينَۗ لِلَّهِ ٱلۡأَمۡرُ مِن قَبۡلُ وَمِنۢ بَعۡدُۚ وَيَوۡمَئِذٖ يَفۡرَحُ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ﴿٤﴾
بِنَصۡرِ ٱللَّهِۚ يَنصُرُ مَن يَشَآءُۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٥﴾

**2-5.** ሮሞች (በፋሪስ) ተሸነፉ። በጣም (ለዐረቡ ዓለም) ቅርብ በሆነችው ምድር ላይ እነርሱም ከመሸነፋቸው በኋላ ያሸንፋሉ። በጥቂት አመታት ውስጥ (ያሸንፋሉ)። ትእዛዙ (ጉዳዩ) በፊትም ሆነ በኋላ የአላህ ነውና። በዚያ ቀንም ምዕምናን ይደሰታሉ። በአላህ እርዳታ ይደሰታሉ። አላህ የሚሻውን ሰው ይረዳል። እርሱም አሸናፊና አዛኝ ነው።

ከሩም ምዕራፍ ከ (1-2) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ኪሥራ የተባለው የፋርስ መንግስት ሸህሪን የተባለ የጦር አበጋዝ የሚመራው ከፍተኛ ጦር ወደ ሮም፤ የሮም መንግስት ደግሞ ዮሐንስ የተባለው የጦር አበጋዝ አስመርቶ ጦሩን ልኮ ነበርና በበስራ እና በአዝርዓት ሁለቱ ተገናኝተው ፋርስች ሮሞችን አሸንፈው ድል በድል መሆናቸው በነብዩ መሐመድ (ﷺ) እና በሙስሊሞች ዘንድ ሲሰማ ነብዩ የሆነውም ይሁን መፅሐፍ አለን የሚሉ ሰዎች በጣዖት አምላኪዎች ሊጠይቁ አይፈልጉም ነበርና ሲያዝኑ ለማፅናናት ነው የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَعۡدَ ٱللَّهِۖ لَا يُخۡلِفُ ٱللَّهُ وَعۡدَهُۥ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٦﴾
يَعۡلَمُونَ ظَٰهِرٗا مِّنَ ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَهُمۡ عَنِ ٱلۡأٓخِرَةِ هُمۡ غَٰفِلُونَ ﴿٧﴾
أَوَلَمۡ يَتَفَكَّرُواْ فِيٓ أَنفُسِهِمۗ مَّا خَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَآ إِلَّا بِٱلۡحَقِّ
وَأَجَلٖ مُّسَمّٗىۗ وَإِنَّ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلنَّاسِ بِلِقَآيِٕ رَبِّهِمۡ لَكَٰفِرُونَ ﴿٨﴾

**6-8.** አላህ እርዳታን በቁርጥ ቀጠረ። አላህ ቀጠሮውን አያፈርስም። ግን አብዛሀኞች ሰዎች አያውቁም። ከቅርቢቱ ህይወት ግልፁን ብቻ ያውቃሉ። እነርሱም ከኋለኛይቱ ዓለም ፍፁም ዘንጊዎች ናቸው። በነፍሶቻቸው ሁኔታ አያስተውሉምን?ሰማያትን፣ ምድርንና በመካከላቸው ያለውን ሁሉ በእውነትና በተወሰነ ጊዜ እንጂ አልፈጠራቸውም። ከሰዎች መካከል ብዙዎቹ ከጌታቸው ጋር በመገናኘት ከሓዲያን ናቸው።

أَوَلَمْ يَسِيرُواْ فِي ٱلْأَرْضِ فَيَنظُرُواْ كَيْفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْۚ كَانُوٓاْ أَشَدَّ مِنْهُمْ قُوَّةً وَأَثَارُواْ ٱلْأَرْضَ وَعَمَرُوهَآ أَكْثَرَ مِمَّا عَمَرُوهَا وَجَآءَتْهُمْ رُسُلُهُم بِٱلْبَيِّنَٰتِۖ فَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيَظْلِمَهُمْ وَلَٰكِن كَانُوٓاْ أَنفُسَهُمْ يَظْلِمُونَ ﴿٩﴾ ثُمَّ كَانَ عَٰقِبَةَ ٱلَّذِينَ أَسَٰٓـُٔواْ ٱلسُّوٓأَىٰٓ أَن كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَكَانُواْ بِهَا يَسْتَهْزِءُونَ ﴿١٠﴾

**9-10.** በምድር ላይ አይሄዱምና የእነዚያን ከበፊታቸው የበሩትን ሰዎች ፍፃሜ እንዴት እንደነበር አይመለከቱምን? በኃይል ከእነርሱ ይበልጡ ነበሩ። ምድርንም አረሱ። እነዚህ ከአለሟትም የበለጠ አለሟት። መልዕክተኞቻቸውም በተአምራቶች መጡባቸው። ግና አስተባበሉና ጠፉ። አላህም የሚበድላቸው አልነበረም። ግና ነፍሶቻቸውን በራሳቸው ይበድሉ ነበር። ከዚያ የእነዚያ ያጠፉት ሰዎች መጨረሻ በአላህ አንቀፆች በማስተባበላቸውና በእርሷ የሚሳሳቁ (የሚያፌዙ) በመሆናቸው ምክንያት መጥፎ ቅጣት ሆነች።

ٱللَّهُ يَبْدَؤُاْ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ ثُمَّ إِلَيْهِ تُرْجَعُونَ ﴿١١﴾

**11.** አላህ መፍጠርን ይጀምራል። ከዚያ ይመልሰዋል። ከዚያ ወደ እርሱ ትመለሳለችሁ።

وَيَوْمَ تَقُومُ ٱلسَّاعَةُ يُبْلِسُ ٱلْمُجْرِمُونَ ﴿١٢﴾
وَلَمْ يَكُن لَّهُم مِّن شُرَكَآئِهِمْ شُفَعَٰٓؤُاْ وَكَانُواْ بِشُرَكَآئِهِمْ كَٰفِرِينَ ﴿١٣﴾

**12-13.** ሰዓቲቱም በምትቆምበት ቀን አመፀኞች ጭጭ ይላሉ (ተስፋ ይቆርጣሉ)። ለእነርሱም ከሚያጋሯቸው ጣዖታት አማላጆች አይኖሩዋቸውም። በሚያጋሯቸውም ጣዖታት ከሓዲያን ይሆናሉ።

وَيَوْمَ تَقُومُ ٱلسَّاعَةُ يَوْمَئِذٍ يَتَفَرَّقُونَ ﴿١٤﴾

**14.** ሰዓቲቱ በምትቆምበት ቀንም በዚያ ቀን ይለያያሉ።

فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَهُمۡ فِي رَوۡضَةٖ يُحۡبَرُونَ ١٥ وَأَمَّا ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ
وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَلِقَآيِٕ ٱلۡأٓخِرَةِ فَأُوْلَٰٓئِكَ فِي ٱلۡعَذَابِ مُحۡضَرُونَ ١٦

**15-16.** እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን ስራዎች የሰሩትማ እነርሱ በገነት ጨፌ ውስጥ ይደሰታሉ፡፡ እነዚያ በአላህ የካዱትማ በአንቀፆቻችንና በኋለኛይቱም ዓለም መገናኘት ያስተባበሉት እነዚያ በቅጣት ውስጥ የሚጣዱ ናቸው፡፡

فَسُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ حِينَ تُمۡسُونَ وَحِينَ تُصۡبِحُونَ ١٧ وَلَهُ ٱلۡحَمۡدُ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ
وَعَشِيّٗا وَحِينَ تُظۡهِرُونَ ١٨

**17-18.** አላህን በምታመሹና በምታነጉም ጊዜ አጥሩት፡፡ ስገዱለት፡፡ ምስጋናም በሰማያትና በምድርም ውስጥ ለእርሱ ብቻ የተገባው ነው፡፡ በሰርክም በቀትር ውስጥ በምትገቡም ጊዜ አጥሩት፡፡

يُخۡرِجُ ٱلۡحَيَّ مِنَ ٱلۡمَيِّتِ وَيُخۡرِجُ ٱلۡمَيِّتَ مِنَ ٱلۡحَيِّ وَيُحۡيِ ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَاۚ
وَكَذَٰلِكَ تُخۡرَجُونَ ١٩

**19.** ህያውን ከሙት ያወጣል፡፡ ሙትንም ከህያው ያወጣል፡፡ ምድርንም ከሞተች በኋላ ህያው ያደርጋታል፡፡ ልክ እንደዚሁም (ከመቃብር) ትወጣላችሁ፡፡

وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنۡ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٖ ثُمَّ إِذَآ أَنتُم بَشَرٞ تَنتَشِرُونَ ٢٠

**20.** እናንተንም ከዐፈር መፍጠሩ ከዚያ እናንተ ወዲያውኑ የምትበታተኑ ሰዎች መሆናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡

وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنۡ خَلَقَ لَكُم مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ أَزۡوَٰجٗا لِّتَسۡكُنُوٓاْ إِلَيۡهَا وَجَعَلَ بَيۡنَكُم مَّوَدَّةٗ
وَرَحۡمَةًۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٢١

**21.** ለእናንተ ከነፍሶቻችሁ (ከጎሶቻችሁ) ሚስቶችን ወደ እነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶች ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚያስተውሉ ህዝቦች ሁሉ አያሌ ተዐምራት አሉበት፡፡

وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦ خَلۡقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱخۡتِلَٰفُ أَلۡسِنَتِكُمۡ وَأَلۡوَٰنِكُمۡۚ
إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّلۡعَٰلِمِينَ ٢٢

22. ሰማያትንና ምድርን መፍጠሩ የቋንቋዎቻችሁና የመልኮቻችሁም መለያየት ከአስደናቂ ምልክቶች ነው። በዚህ ውስጥ ለዐዋቂዎች ታዐምራቶች አሉበት።

وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ مَنَامُكُم بِٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ وَٱبْتِغَآؤُكُم مِّن فَضْلِهِۦٓ ۚ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَسْمَعُونَ ﴿٢٣﴾

23. በሌሊትም ሆነ በቀን መተኛታችሁ ከችሮታውም መፈለጋችሁ ከምልክቶች ነው። በዚህ ውስጥ ለሚሰሙ ህዝቦች ብዙ ሁሉ ታዐምራት አሉበት።

وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦ يُرِيكُمُ ٱلْبَرْقَ خَوْفًا وَطَمَعًا وَيُنَزِّلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً
فَيُحْىِۦ بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَآ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿٢٤﴾

24. ብልጭታንም ፈሪዎችና ከጃዮች ስትሆኑ ለእናንተ ማሳየቱ ከሰማይም ውሃን ማውረዱ በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ህያው ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው። በዚህ ውስጥ ለሚያስቡ ህዝቦች ሁሉ አያሌ ታዐምራት አሉበት።

وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَن تَقُومَ ٱلسَّمَآءُ وَٱلْأَرْضُ بِأَمْرِهِۦ ۚ
ثُمَّ إِذَا دَعَاكُمْ دَعْوَةً مِّنَ ٱلْأَرْضِ إِذَآ أَنتُمْ تَخْرُجُونَ ﴿٢٥﴾

25. ሰማይና ምድርም ያለ ምሰሶ በትእዛዙ መቆማቸው ከዚያ (መልአክ ለትንሳኤ) ከምድር ጥሪን በጠራችሁ ጊዜ እናንተ ወዲያውኑ የምትወጡ መሆናችሁ ከአስደናቂ ምልክቶች ነው።

وَلَهُۥ مَن فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ كُلٌّ لَّهُۥ قَٰنِتُونَ ﴿٢٦﴾ وَهُوَ ٱلَّذِى يَبْدَؤُا۟ ٱلْخَلْقَ ثُمَّ يُعِيدُهُۥ
وَهُوَ أَهْوَنُ عَلَيْهِ ۚ وَلَهُ ٱلْمَثَلُ ٱلْأَعْلَىٰ فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٢٧﴾

26-27. በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። ሁሉም ለእርሱ ታዛዦች ናቸው። እርሱ ያ! መፍጠርን የሚጀምር (የሚያስገኝ) ከዚያ የሚመልሳቸው ብቸኛ አምላክ ነው። እርሱ (መመለሱ) በእርሱ ላይ በጣም ቀላል ነው። ለእርሱም በሰማያትና በምድር ባህሪይ አንድነትና ለእርሱ ብጤ የሌለው በመሆን ከፍተኛ ምሳሌ አለው። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

ضَرَبَ لَكُم مَّثَلًا مِّنْ أَنفُسِكُمْۖ هَل لَّكُم مِّن مَّا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُكُم مِّن شُرَكَآءَ فِى مَا رَزَقْنَٰكُمْ فَأَنتُمْ فِيهِ سَوَآءٌ تَخَافُونَهُمْ كَخِيفَتِكُمْ أَنفُسَكُمْۚ كَذَٰلِكَ نُفَصِّلُ ٱلْءَايَٰتِ لِقَوْمٍ يَعْقِلُونَ ﴿٢٨﴾ بَلِ ٱتَّبَعَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُوٓا۟ أَهْوَآءَهُم بِغَيْرِ عِلْمٍۖ فَمَن يَهْدِى مَنْ أَضَلَّ ٱللَّهُۖ وَمَا لَهُم مِّن نَّٰصِرِينَ ﴿٢٩﴾

**28-29.** ለእናንተ ከነፍሶቻችሁ የሆነን ምሳሌ አደረገላችሁ። እርሱም እጆቻችሁ ከያዟቸው ባሮች ውስጥ በሰጠናችሁ ፀጋ ለእናንተ ተጋሪዎች አሏችሁን? ታዲያ እናንተና እነርሱ በእርስ ትክክል ናችሁን? ነፍሶቻችሁን (ብጤዎቻችሁን) እንደምትፈሩ ትፈሩዋቸዋላችሁን? እንደዚሁ ለሚያስተውሉ ህዝቦች አንቀፆችን እንገልጻለን። ይልቁንም እነዚያ የበደሉ ሰዎች ያለ ዕውቀት ዝንባሌዎቻቸውን ተከተሉ። አላህም ያጠመመውን ሰው የሚያቀናው ማነው? ለእነርሱም ከረዳቶች ምንም የላቸውም። የሰሩትማ እነርሱ በገነት ጨፌ ውስጥ ይደሰታሉ።

ከሩም ምዕራፍ (28) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ ሰዎች በሐጅም ሆነ በዑምራ ተልቢያ ሲያደርጉ ለበይክ ላሸሪከለክ ኢላ ሸሪከን ሁወ ለከ ተመሊኩሁ ወማ መለከ ይሉ ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ حَنِيفًاۚ فِطْرَتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى فَطَرَ ٱلنَّاسَ عَلَيْهَاۚ لَا تَبْدِيلَ لِخَلْقِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ ٱلدِّينُ ٱلْقَيِّمُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٠﴾ ۞ مُنِيبِينَ إِلَيْهِ وَٱتَّقُوهُ وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَلَا تَكُونُوا۟ مِنَ ٱلْمُشْرِكِينَ ﴿٣١﴾ مِنَ ٱلَّذِينَ فَرَّقُوا۟ دِينَهُمْ وَكَانُوا۟ شِيَعًاۖ كُلُّ حِزْبٍۭ بِمَا لَدَيْهِمْ فَرِحُونَ ﴿٣٢﴾

**30-32.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እውነት ተዘንባይ ሆነህም ፊትህን ለሃይማኖት ቀጥ አድርግ። የአላህን ፍጥረት ያችን አላህ ሰዎችን በርስዋ ላይ የፈጠረባትን (ሃይማኖት) ያዙዋት የአላህን ፍጥረት መለወጥ የለም። ይህ ቀጥተኛ ሃይማኖት ነው። ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም። ወደ እርሱ ተመላሾች ሆናችሁ (የአላህን ሃይማኖት ያዙ)። ፍሩትም ሶላትንም አስተካክላችሁ ስገዱ ከአጋሪዎችም አትሁኑ። ከእነዚያ ሃይማኖታቸውን ከለያዩትና ክፍልፍልም ከሆኑት (አትሁኑ) ህዝብ ሁሉ እነርሱ ዘንድ ባለው ነገር ተደሳቾች ናቸው።

**ከሩም ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-32) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የኢስላምን ትክክለኛነት ማረጋገጥ፤
2. የመፅሐፍ ባለቤቶች ከከሓዲያን ኮሚኒስቶች ይልቅ ለሙስሊሞች የተሻሉና በአስተሳሰብ የቀረቡ ስለመሆናቸው፤
3. ብዙ ሰዎች ለአኼራ የሚሆናቸውን ነገር በትክክል ለይተው እንደማያውቁ፤
4. ሰዎች በዘመናዊ ትምህርት ቢመጥቁም በመንፈሳዊ ትምህርት ካልተጠናከሩ በስተቀር ፋይዳ እንደሌላቸው
5. የሙቶ መነሳትን ትክክለኛት ማረጋገጥ፤ ብዙ ሰዎች በማስረጃ የተረጋገጠውን ሙቶ መነሳትን
6. በምድር ላይ መንቀሳቀስና ሪዝቅን መፈለግ ተገቢ እና የተፈቀደ መሆኑን፤
7. የአጥፊዎች ምንዳ አስከፊ እንደሚሆን፤
8. በሸሪዓ በቁርኣን ማፌዝ ክህደት እንደሆነ፤
9. የአላህን ብቸኛ አምላክነት ለማመን ሌላ ሳያስፈልግ ማንም ሰው የራሱን አፈጣጠር ብቻ መመልከቱ በቂ መሆኑን፤
10. ይህች ዐለም በሙሉ ለቁም ነገር የተፈጠረችና ማብቂያዋም የተወሰነ ስለመሆኑ፤
11. ሰዎች በዚህች ምድር ሲኖሩ የሚገጥማቸው ችግር ሁሉ በጥፋታቸው ምክንያት መሆኑን፤
12. የቂያማ ዕለት ለከሓዲያንም ሆነ ለአጋሪ ሰው ሽምግልና ተቀባይነት እንደሌለው፤
13. በቂያማ ዕለት አማኞች ሲደሰቱ ከሓዲያን ደግሞ እንደሚዋረዱ፤
14. በጀነት ውስጥ መዝናኛዎችና መደሰቻዎች ያሉ መሆኑን፤
15. በቂያማ ዕለት በዚህች ዐለም የነበሩት ቅጥፈቶች ሁሉ ጠፍተው እውነት ብቻ እደሚቀር፤
16. አላህን ከማይገቡት ነገሮች ሁሉ ማፅዳት ግዴታ ስለመሆኑ፤
17. ለፀጋዎቹ ሁሉ አላህን ማመስገን ግዴታ ስለመሆኑ፤
18. የአምስቱን ወቅት ሶላቶች መስገድ ግዴታ ስለመሆኑ፤
19. ሰማይ፤ ምድር፤ የሰው ልጆች መግባቢያ የሆነው ቋንቋና የመልካቸው መለያየት ራሱ ትልቅ ተዐምር መሆኑን፤
20. በብሄር ብሄረሰቦች መከፋፈላችን እምነታዊ ጠቀሜታ እንዳለው፤
21. ሌትም ሆነ ቀን መተኛት እንደሚቻል፤
22. እንቅልፍ ራሱ ሙቶ የመነሳት ሐቅ መኖሩን የሚያሳይ ዋና መረጃ መሆኑን፤
23. ምድር በዝናብ ምክንያት ሂወት መዝራቷ ሙቶ መነሳት ሐቅ መሆኑን ከሚያሥረዱ አንዱ መሆኑን እንማራለን።

وَإِذَا مَسَّ ٱلنَّاسَ ضُرٌّ دَعَوْاْ رَبَّهُم مُّنِيبِينَ إِلَيْهِ ثُمَّ إِذَآ أَذَاقَهُم مِّنْهُ رَحْمَةً إِذَا فَرِيقٌ مِّنْهُم
بِرَبِّهِمْ يُشْرِكُونَ ٣٣ لِيَكْفُرُواْ بِمَآ ءَاتَيْنَٰهُمْ ۚ فَتَمَتَّعُواْ فَسَوْفَ تَعْلَمُونَ ٣٤ أَمْ أَنزَلْنَا
عَلَيْهِمْ سُلْطَٰنًا فَهُوَ يَتَكَلَّمُ بِمَا كَانُواْ بِهِۦ يُشْرِكُونَ ٣٥

**33-35.** ሰዎችንም ችግር ባገኛቸው ጊዜ ጌታቸውን ወደ እርሱ ተመላሾች ሆነው ይጠሩታል። ከዚያም ከርሱ ችሮታንም ባቀመሳቸው ጊዜ ከእነርሱ ከፊሎች ወዲያውኑ በጌታቸው ጣዖትን ያጋራሉ። በሰጠናቸው ፀጋ ሊክዱ

(ያጋሩ)። ተጣቀሙም። በእርግጥም መጨረሻችሁን ወደፊት ታውቃላችሁ። በእነርሱ ላይ አላህ አስረጅን አወረድን? ታድያ እርሱ በነዚያ በእርሱ ያጋሩ በነበሩት ነገር ይናገራልን? የለም።

وَإِذَآ أَذَقۡنَا ٱلنَّاسَ رَحۡمَةٗ فَرِحُواْ بِهَاۖ وَإِن تُصِبۡهُمۡ سَيِّئَةُۢ بِمَا قَدَّمَتۡ أَيۡدِيهِمۡ إِذَا هُمۡ يَقۡنَطُونَ ٣٦
أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّ ٱللَّهَ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقۡدِرُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ٣٧

**36-37.** ሰዎችንም ችሮታን ባቀመስናቸው ጊዜ በእርሷ ይደሰታሉ፤ እጆቻቸውም ባሳለፉት ምክንያት መከራ ብታገኛቸው ወዲያውኑ እነርሱ ተስፋ ይቆርጣሉ። አላህ ለሚሻው ሰው ሲሳይን የሚያሰፋ የሚያጠብም መሆኑን አያዩምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑ ህዝቦች አስደናቂ ምልክቶች አሉበት።

فَـَٔاتِ ذَا ٱلۡقُرۡبَىٰ حَقَّهُۥ وَٱلۡمِسۡكِينَ وَٱبۡنَ ٱلسَّبِيلِۚ ذَٰلِكَ خَيۡرٞ لِّلَّذِينَ يُرِيدُونَ وَجۡهَ ٱللَّهِۖ
وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ٣٨

**38.** (አማኝ ሆይ!) የዝምድናን ባለቤት ተገቢውን ስጠው። ለድሃና ለመንገደኛም እርዳ። ይህ ለእነዚያ የአላህን ፊት ለሚሹ ሁሉ መልካም ነው። እነዚያም እነርሱም በሁለተኛው ዓለም የፈለጉትን የሚያገኙ ምርጥ ክፍሎች ናቸው።

وَمَآ ءَاتَيۡتُم مِّن رِّبٗا لِّيَرۡبُوَاْ فِيٓ أَمۡوَٰلِ ٱلنَّاسِ فَلَا يَرۡبُواْ عِندَ ٱللَّهِۖ وَمَآ ءَاتَيۡتُم مِّن زَكَوٰةٖ
تُرِيدُونَ وَجۡهَ ٱللَّهِ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُضۡعِفُونَ ٣٩

**39.** (ሰዎች ሆይ!) ከበረከትም በሰዎች ገንዘቦች ውስጥ ይጨመር ዘንድ በማቀድ የምትሰጡት ገንዘብ በአላህ ዘንድ ቅንጣት አይጨምርም። የአላህን ፊት ብቻ የምትሹ ሆናችሁ የምትሰጡት ምጽዋት ግን እነዚያ እውነተኛ ሰጪዎች አበርካቾች እነርሱ ናቸው።

ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ ثُمَّ رَزَقَكُمۡ ثُمَّ يُمِيتُكُمۡ ثُمَّ يُحۡيِيكُمۡۖ هَلۡ مِن شُرَكَآئِكُم مَّن يَفۡعَلُ
مِن ذَٰلِكُم مِّن شَيۡءٖۚ سُبۡحَٰنَهُۥ وَتَعَٰلَىٰ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ٤٠

**40.** አላህ ያ የፈጠራችሁ ከዚያ ሲሳይን የሰጣችሁ ከዚያ የሚገድላችሁ ከዚያ ህያው የሚያደርጋችሁ ነው። ከምታጋሯቸው ጣዖታት ውስጥ ከዚሃችሁ አንዳችን የሚሰራ አለን? ለአላህ ጥራት ይገባው በእርሱ ከሚያጋሩትም ሁሉ ላቀ።

**ከሩም ምዕራፍ ከአንቀፅ (33-40) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *አጋሪዎች ያላቸው ድንቁርና፤*
2. *አላህ በወንጀል ላይ ሙጥኝ ለሚሉ ከሓዲያን ላይ መዛቱን፤*
3. *ሞት ሲመጣ የከሓዲያን ሁኔታ ምን እንደሚመስል፤*
4. *የአላህ ጥበብና ማስተናበር የታየበት ከንውን፤*
5. *አላህ ለፈለገው ሰው በችሮታው ልዩ ልዩ ፀጋዎችን እንደሚለግስለትና የፈለገዉን ደግሞ እንደሚከለክለው፤ ይህም ድርጊት ራሱ ለአላህ መኖር ትልቅ ማስረጃ መሆኑን፤*
6. *ዘመዶች ተገቢውን እንክብካቤ ማግኘት እንዳለባቸው፤*
7. *በሙስሊሙ መካከል የሚኖሩ ድሆችና ችግረኞች በሙስሊሞች መረዳት እንዳለባቸው፤*
8. *የዱንያን ስጦታ አሳልፎ መስጠት እንደሚቻል፤*
9. *ለአላህ ተብሎ የሚሰጥ ሰደቃ አጅሩ እጥፍ ድርብ ስለመሆኑ፤*
10. *አጋሪዎችንና ማጋራትን ማውገዝን፤*

ظَهَرَ ٱلْفَسَادُ فِى ٱلْبَرِّ وَٱلْبَحْرِ بِمَا كَسَبَتْ أَيْدِى ٱلنَّاسِ لِيُذِيقَهُم بَعْضَ ٱلَّذِى عَمِلُوا۟
لَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ﴿٤١﴾

**41.** የሰዎች እጆች በሰሩት ኃጢአት ምክንያት የዚያን የሰሩትን ከፊሉን ያቀምሳቸው ዘንድ መከራው በየብስና በባህር ተገለጠ። (ተሰራጨ) እነርሱ ሊመለሱ ይከጀላልና።

قُلْ سِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَٱنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَـٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلُ ۚ كَانَ أَكْثَرُهُم مُّشْرِكِينَ ﴿٤٢﴾

**42.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በምድር ላይ ሂዱ የነዚያንም በፊት የነበሩት ሰዎች መጨረሻ እንዴት እንደነበረ ተመልከቱ በላቸው። አብዛኞቻቸው አጋሪዎች ነበሩ።

فَأَقِمْ وَجْهَكَ لِلدِّينِ ٱلْقَيِّمِ مِن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ يَوْمٌ لَّا مَرَدَّ لَهُۥ مِنَ ٱللَّهِ ۖ يَوْمَئِذٍ يَصَّدَّعُونَ ﴿٤٣﴾
مَن كَفَرَ فَعَلَيْهِ كُفْرُهُۥ ۖ وَمَنْ عَمِلَ صَـٰلِحًا فَلِأَنفُسِهِمْ يَمْهَدُونَ ﴿٤٤﴾ لِيَجْزِىَ ٱلَّذِينَ
ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ مِن فَضْلِهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ ٱلْكَـٰفِرِينَ ﴿٤٥﴾

**43-45.** ለእርሱ መመለስ የሌለው ቀን የትንሳኤ ቀን ከአላህ ላይ ሳይመጣ በፊት ፊትህን ወደ ቀጥተኛው ሃይማኖት ቀጥ አድርግ በዚያ ቀን ወደ ገነትና ወደ እሳት ይለያያሉ። በአላህ የካደ ሰው የክህደቱ ጠንቁ በእርሱው ላይ ብቻ ነው። መልካምም የሰሩ ሁሉ ለነፍሶቻቸው ማረፊያዎች ያዘጋጃሉ። እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችንም የሰሩትን ከችሮታው ይመነዳ ዘንድ (ይለያያሉ)። እርሱ ከሓዲዎችን አይወድምና።

وَمِنْ ءَايَٰتِهِۦٓ أَن يُرْسِلَ ٱلرِّيَاحَ مُبَشِّرَٰتٍ وَلِيُذِيقَكُم مِّن رَّحْمَتِهِۦ وَلِتَجْرِىَ ٱلْفُلْكُ بِأَمْرِهِۦ
وَلِتَبْتَغُوا۟ مِن فَضْلِهِۦ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ٤٦

**46.** ነፋሶችንም (በዝናብ) ልታያበስራችሁ ከችሮታውም (በእርሷ) ሊያቀምሳችሁ መርከቦችም በትእዛዙ እንዲንሻለሉ ከችሮታውም እንድትፈልጉ ታመሰግኑትም ዘንድ መላኩ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው።

وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ رُسُلًا إِلَىٰ قَوْمِهِمْ فَجَآءُوهُم بِٱلْبَيِّنَٰتِ فَٱنتَقَمْنَا مِنَ ٱلَّذِينَ
أَجْرَمُوا۟ ۖ وَكَانَ حَقًّا عَلَيْنَا نَصْرُ ٱلْمُؤْمِنِينَ ٤٧

**47.** ከአንተ በፊትም መልዕክተኞችን ወደ ህዝቦቻቸው በእርግጥ ላክን። በግልጽ ማስረጃዎችም መጡባቸው። ከእነዚያ ካመፁትም ተበቀልን። ምዕመናኖችንም መርዳት በእኛ ላይ ተገቢ ሆነ።

ٱللَّهُ ٱلَّذِى يُرْسِلُ ٱلرِّيَٰحَ فَتُثِيرُ سَحَابًا فَيَبْسُطُهُۥ فِى ٱلسَّمَآءِ كَيْفَ يَشَآءُ وَيَجْعَلُهُۥ كِسَفًا
فَتَرَى ٱلْوَدْقَ يَخْرُجُ مِنْ خِلَٰلِهِۦ ۖ فَإِذَآ أَصَابَ بِهِۦ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦٓ إِذَا هُمْ يَسْتَبْشِرُونَ ٤٨
وَإِن كَانُوا۟ مِن قَبْلِ أَن يُنَزَّلَ عَلَيْهِم مِّن قَبْلِهِۦ لَمُبْلِسِينَ ٤٩ فَٱنظُرْ إِلَىٰٓ ءَاثَٰرِ رَحْمَتِ ٱللَّهِ
كَيْفَ يُحْىِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَآ ۚ إِنَّ ذَٰلِكَ لَمُحْىِ ٱلْمَوْتَىٰ ۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ٥٠

**48-50.** አላህ ያ ነፋሶችን የሚልክ ነው። ደመናንም ይቀሰቅሳሉ። በሰማይ ላይም እንደሚሻ ይዘረጋዋል ቁርጥራጮችም ያደርገዋል። ዝናቡንም ከደመናው መካከል ሲወጣ ታያለህ። በእርሱም ከባሮቹ የሚሻውን በለየ ጊዜ ወዲያውኑ እነርሱ ይደሰታሉ። በእነርሱም ላይ ከመውረዱ በፊት ከእርሱ በፊት በእርግጥ ተስፋ ቆራጮች ነበሩ። (ተመልካች ሆይ!) ምድርንም ከሞተች በኋላ እንዴት ህያው እንደሚያደርጋት ወደ አላህ ችሮታ ፈለጎች ተመልከት። (ይህ አድራጊ) ሙታንንም በእርግጥ ህያው አድራጊ ነው እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

وَلَئِنْ أَرْسَلْنَا رِيحًا فَرَأَوْهُ مُصْفَرًّا لَّظَلُّوا۟ مِنۢ بَعْدِهِۦ يَكْفُرُونَ ٥١ فَإِنَّكَ لَا تُسْمِعُ ٱلْمَوْتَىٰ
وَلَا تُسْمِعُ ٱلصُّمَّ ٱلدُّعَآءَ إِذَا وَلَّوْا۟ مُدْبِرِينَ ٥٢ وَمَآ أَنتَ بِهَٰدِ ٱلْعُمْىِ عَن ضَلَٰلَتِهِمْ ۖ إِن
تُسْمِعُ إِلَّا مَن يُؤْمِنُ بِـَٔايَٰتِنَا فَهُم مُّسْلِمُونَ ٥٣

**51-53.** ነፋስን በአዝመራዎች ላይ ብንልክና ገርጥቶ ቢያዩት ከእርሱ በኋላ በእርግጥ ችሮታውን የሚክዱ ይሆናሉ፡፡ አንተም ሙታንን አታሰማም ደንቆሮዎችንም ዟሪዎች ሆነው በሸሹ ጊዜ ጥሪን አታሰማም፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ እውሮችንም ከጥመታቸው የምታቀና አይደለህም፡፡ በአንቀፆቻችን የሚያምኑትን ሰዎች እንጂ ሌላን አታሰማም እነርሱም ታዛዦች ናቸው፡፡

۞ ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن ضَعْفٍ ثُمَّ جَعَلَ مِنۢ بَعْدِ ضَعْفٍ قُوَّةً ثُمَّ جَعَلَ مِنۢ بَعْدِ قُوَّةٍ
ضَعْفًا وَشَيْبَةً ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَآءُ ۖ وَهُوَ ٱلْعَلِيمُ ٱلْقَدِيرُ ٥٤

**54.** አላህ ያ ከደካማ ፍትወት ጠብታ የፈጠራችሁ ነው፤ ከዚያ ከደካማነት በኋላ ኃይልን አደረገ ከዚያ ከብርቱነት በኋላ ደካማነትና ሽበትን አደረገ የሚሻውን ይፈጥራል፡፡ እርሱም ዐዋቂው ቻዩ ነው፡፡

وَيَوْمَ تَقُومُ ٱلسَّاعَةُ يُقْسِمُ ٱلْمُجْرِمُونَ مَا لَبِثُوا۟ غَيْرَ سَاعَةٍ ۚ كَذَٰلِكَ كَانُوا۟ يُؤْفَكُونَ ٥٥
وَقَالَ ٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْعِلْمَ وَٱلْإِيمَـٰنَ لَقَدْ لَبِثْتُمْ فِى كِتَـٰبِ ٱللَّهِ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْبَعْثِ ۖ
فَهَـٰذَا يَوْمُ ٱلْبَعْثِ وَلَـٰكِنَّكُمْ كُنتُمْ لَا تَعْلَمُونَ ٥٦ فَيَوْمَئِذٍ لَّا يَنفَعُ ٱلَّذِينَ
ظَلَمُوا۟ مَعْذِرَتُهُمْ وَلَا هُمْ يُسْتَعْتَبُونَ ٥٧

**55-57.** ሰዓቲቱ በምትከሰትበት ቀን ከሓዲያን ከአንዲት ሰዓት በስተቀር በመቃብር (በዱንያ) አልቆየንም ብለው ይምላሉ፡፡ ልክ እንደዚሁ በዚህኛው ዐለምም እያሉ ከእውነት ይመለሱ ነበር፡፡ እነዚያም እውቀትንና እምነትን የተሰጡት በአላህ መጽሐፍ ፍርድ እስከ ትንሳኤ ቀን በእርግጥ ቆያችሁ ይህም የካዳችሁት የትንሳኤ ቀን ነው፡፡ ግን እናንተ የማታውቁ ነበራችሁ ይሏቸዋል፡፡ በዚያም ቀን እነዚያን የበደሉትን ማመካኘታቸው አይጠቅማቸውም፡፡ እነርሱም በወቀሳ አይታለፉም፡፡

وَلَقَدْ ضَرَبْنَا لِلنَّاسِ فِى هَـٰذَا ٱلْقُرْءَانِ مِن كُلِّ مَثَلٍ ۚ وَلَئِن جِئْتَهُم بِـَٔايَةٍ لَّيَقُولَنَّ ٱلَّذِينَ
كَفَرُوٓا۟ إِنْ أَنتُمْ إِلَّا مُبْطِلُونَ ٥٨ كَذَٰلِكَ يَطْبَعُ ٱللَّهُ عَلَىٰ قُلُوبِ ٱلَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ ٥٩
فَٱصْبِرْ إِنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّ ۖ وَلَا يَسْتَخِفَّنَّكَ ٱلَّذِينَ لَا يُوقِنُونَ ٦٠

**58-60.** በዚህም ቁርኣን ውስጥ ለሰዎች የምሳሌ አይነቶችን ሁሉ በእርግጥ ገለጽን። በተዐምርን ብትመጣላቸው እንኳን እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች እናንተ አበላሺዎች የጥፋት ተጣሪ ዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም ይላሉ። ልክ እንደዚሁ አላህ በነዚያ በማያውቁት ሰዎች ልቦች ላይ ያትማል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስለዚህ ታገሥ። የአላህ ቀጠሮ እውነት ነውና። እነዚያም በትንሳኤ የማያረጋግጡት ሰዎች አያቅልሉህ።

**ከሩም ምዕራፍ ከአንቀፅ (41-60) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ድርቅና ረሀብ የወንጀልና ሽርክ ውጤቶች ስለመሆናቸው፤
2. ኢስላምን አክብሮ መያዝ አማራጭ የሌለው ግዴታ ስለመሆኑ፤
3. ስለትንሳኤ ቀን ማሰብ አስፈላጊ መሆኑን፤
4. አላህ ከሓዲያንን እንደሚጠላና አማኞችን እንደሚወድ
5. የአላህን ጌትነት ማረጋገጥ፤
6. አላህ በባሮቹ ላይ ለሚያሳያቸው ፀጋዎች ሁሉ ማመስገን እንዳለበት፤
7. አላህ ዘመኑ ቢረዝምም ከከሓዲያን መበቀሉና ለሙስሊሞች መርዳቱ አይቀሬ ስለ መሆኑ፤
8. ሙስሊሞች በአላህ ላይ በፍቃዱ የሰጣቸው መብት እንዳላቸው፤
9. ነብይነት በነብዩ (ﷺ) የተጀመረ ሳይሆን በሳቸው የተዘጋ መሆኑን፤
10. ከነብዩ (ﷺ) መላክ በፊት የነበሩ ነብያት ለተወሰኑ ሕዝቦች ብቻ ይላኩ እንደነበር፤
11. ሙቶ መነሳትን በልዩ ልዩ ማስረጃዎች ማረጋገጥ፤
12. አላህ ዝናብን እንዴት እንደሚፈጥር፤
13. በችግርም ጊዜ ሆነ በደስታ የከሓዲያን ሁኔታ ምን እንደሚመስል፤
14. ከተጨባጭ ነገር በመነሳት ሩቅን ማመን እንደሚቻል፤
15. ከሓዲያን በህይወት እያሉ ሙታን እንደሆኑ፤
16. የነብያትንም ሆነ የምሁራንን አስተምህሮትና መልካም ጥረት በጥሞና የሚሰሙትና በተግባር ላይ የሚያዉሉት አማኞች ብቻ መሆናቸዉን፤
17. የሰው ልጅ ከፅንሰት እስከ አረጋዊነት ያሳለፋቸው ሂደቶች ማውሳቱ፤
18. የእውቀትንና የእምነትን ትልቅነት መግለፅ፤
19. የግፈኞች ምክንያቶች ተቀባይነት እንደሌለው፤
20. የሰው ልጅ አስከፊ ሁኔታው ወንጀሉ በዝቶ ልቡን ሲደፍንበት መሆኑን፤
21. ትዕግስትና አስተዋይነት አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
22. ነብዩም (ﷺ) ሆኑ ተከታዮቻቸው አላዋቂዎች በሚሉት ሊበሳጩ እንደማይገባ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የሩም ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (31)
# የሉቅማን ምዕራፍ
## (ሱረቱ ሉቅማን)

سُورَةُ لُقۡمَانَ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (34) ናቸው።**

**የሱረቱ ሉቅማን መግቢያ**

ስለ ቁርኣንና በውስጡ ስላለው ታላቅ ተልዕኮ በማውሳት ይጀምርና የአጥማሚዎችን ባህሪ ያብራራል። አማኞችን በጀነት አብስሮ የአላህን ፍጥረት በአንክሮ እንድንመለከት ግፊት ያሳድራል። አጋሪዎች ባዕድ አምላክ ያጋሩበት አላህ ከእሱ ሌላ ማንም ሊፈጥረው የማይችለውን ፍጡር እንደፈጠረ ያስተምርና የሉቅማነል ሐኪም ምክሮችን ይደረድራል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓ ۝١ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡحَكِيمِ ۝٢ هُدٗى وَرَحۡمَةٗ لِّلۡمُحۡسِنِينَ ۝٣ ٱلَّذِينَ يُقِيمُونَ
ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَهُم بِٱلۡأٓخِرَةِ هُمۡ يُوقِنُونَ ۝٤ أُوْلَٰٓئِكَ عَلَىٰ هُدٗى مِّن رَّبِّهِمۡۖ
وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ۝٥

**1-5.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም፤* ይህ ምእራፍ ጥበብ ከተሞላው መፅሐፍ አንቀፆች አንዱ ነው። ለበጎ አድራጊዎች ሁሉ መሪ፣ እዝነት ስትሆን፣ ለእነዚያ ሶላትን አስተካክለው ለሚሰግዱ፣ ዘካንም ለሚሰጡት፤ በመጨረሻይቱ ዓለም የሚያረጋግጡ ለሆኑት፤ እነዚያ (የተጠቀሱትን ባህሪያት የሚላበሱ ሰዎች ሁሉ) በጌታቸው መመሪያ ላይ የሚጓዙ ናቸው። ፍላጎታቸውንም ያገኙትም እነርሱ ብቻ ናቸው።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፩ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يَشۡتَرِي لَهۡوَ ٱلۡحَدِيثِ لِيُضِلَّ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ بِغَيۡرِ عِلۡمٖ وَيَتَّخِذَهَا هُزُوًاۚ
أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عَذَابٞ مُّهِينٞ ۝٦ وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِ ءَايَٰتُنَا وَلَّىٰ مُسۡتَكۡبِرٗا كَأَن لَّمۡ يَسۡمَعۡهَا
كَأَنَّ فِيٓ أُذُنَيۡهِ وَقۡرٗاۖ فَبَشِّرۡهُ بِعَذَابٍ أَلِيمٖ ۝٧

**6-7.** ከሰዎች መካከል ያለ ምንም እውቀት ሰዎችን ከአላህ መንገድ ሊያሳስትና የአላህን መንገድ ማላገጫ አድርጎ ሊይዝ፣ አታላይ ወሬን የሚገዛ አለ። እነዚያ (ይህን የሚያደርጉ) ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አለላቸው።* አንቀፆቻችን በእርሱ ላይ በሚነበቡ ጊዜ እንዳልሰማትና በጆሮቹ ድንቁርና እንዳለበት የኮራ ሆኖ ይዞራል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህን ሰው በአሳማሚ ቅጣት አብስረው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ዓሚር ወይም አቡ ማሊክ አል. አሽዐሪይ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «ከኔ ተከታዮች መካከል ዝሙት መፈፀምን፣ የሀር ልብስ መልበስን፣ የአልኮል መጠጦችን መጠጣትንና የሙዚቃ መሳሪያዎችን መጠቀምን የሚፈቅዱ ሰዎች ይኖራሉ። ከነርሱም መካከል አንድ ተራራ ጫፍ ላይ የሚኖሩ ሰዎች አሉ። ምሽት ላይ ከብቶቻቸውና በጎቻቸውን የሚጠብቅላቸው ሰው ከብቶቻቸውንና በጎቻቸውን ይዞ ወደነርሱ ከመጣ በኋላ ስለ አንዳች ነገር ይጠይቃቸዋል። እነርሱም «ነገ ተመለስልን» ይሉታል። አላህም እነዚህን ሰዎች ለሊቱን ያጠፋቸዋል። ተራራውንም በነርሱ ላይ ይጥለዋል። እንዲሁም የተቀሩትን ወደ ጦጣነትና ወደ አሳማነት ይቀይራቸዋል። እስከ ትንሳኤ ቀንም እንዲሁ ይቆያሉ»

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمْ جَنَّٰتُ ٱلنَّعِيمِ ﴿٨﴾
خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقًّاۚ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٩﴾

**8-9.** እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካሞችን ተግባራት የሰሩ ሰዎች ሁሉ ለእነርሱ የፀጋ ገነቶች አሏቸው። በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች ሲሆኑ። አላህ እውነተኛን የተስፋ ቃል ገባላቸው። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ بِغَيْرِ عَمَدٍ تَرَوْنَهَاۖ وَأَلْقَىٰ فِى ٱلْأَرْضِ رَوَٰسِىَ أَن تَمِيدَ بِكُمْ وَبَثَّ فِيهَا مِن
كُلِّ دَآبَّةٍۚ وَأَنزَلْنَا مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَنۢبَتْنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوْجٍ كَرِيمٍ ﴿١٠﴾ هَٰذَا خَلْقُ ٱللَّهِ
فَأَرُونِى مَاذَا خَلَقَ ٱلَّذِينَ مِن دُونِهِۦۚ بَلِ ٱلظَّٰلِمُونَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿١١﴾

**10-11.** ሰማያትን ያለ ምሰሶዎች እንደምታዩዋት ሁሉ ፈጠረ። በምድርም ውስጥ በእናንተ እንዳታረገርግ ተራራዎችን ጣለ። በእርሷም ላይ ከተንቀሳቃሽ ነገሮች ሁሉ በተነ። ከሰማይም ውሃን አወረድን። በእርሷ ውስጥ ከመልካም ዓይነት ሁሉ ቡቃያን አበቀልን። ይህ የአላህ ፍጡር ነው። እነዚያ ከእርሱ ሌላ ያሉት ምንን እንደ ፈጠሩ እስኪ አሳዩኝ። በዳዮች በእውነት በግልጽ ጥመት ውስጥ ናቸው።

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا لُقْمَٰنَ ٱلْحِكْمَةَ أَنِ ٱشْكُرْ لِلَّهِ ۚ وَمَن يَشْكُرْ فَإِنَّمَا يَشْكُرُ لِنَفْسِهِۦ ۖ
وَمَن كَفَرَ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِىٌّ حَمِيدٌ ﴿١٢﴾

**12.** ለሉቅማንም* ጥበብን በእርግጥ ሰጠነው። አላህን አመስግን አልነውም። ያመሰገነም ሰው የሚያመሰግነው ለራሱ ብቻ ነው። የካደም ሰው በራሱ ላይ ነው። አላህ ተብቃቂና ምስጉን ነውና።

* ሉቅማን ጥበብን የተሰጠ መልካምና ምርጥ የአላህ ሰው ነው

وَإِذْ قَالَ لُقْمَٰنُ لِٱبْنِهِۦ وَهُوَ يَعِظُهُۥ يَٰبُنَىَّ لَا تُشْرِكْ بِٱللَّهِ ۖ إِنَّ ٱلشِّرْكَ لَظُلْمٌ عَظِيمٌ ﴿١٣﴾

**13.** ሉቅማንም ለልጁ እርሱ የሚገስፀው ሲሆን ልጄ ሆይ! በአላህ ጣኦትን አታጋራ። ማጋራት ታላቅ በደል* ነውና (ያለውን አስታውስ)።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻህ እንዳስተላለፉት«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግል ከስራዎች ሁሉ የበለጠ ሆኖ እናየዋለንና እኛ ሴቶች አንታገልምን?»በማለት ጠየቅኋቸው። እሳቸውም«አዎን ለሴቶች ከሁሉም በላጭ የሆነ ትግል ማለት በአላህ ዘንድ ተቀባይነት ያለውን ሐጅ መፈፀም ነው»

وَوَصَّيْنَا ٱلْإِنسَٰنَ بِوَٰلِدَيْهِ حَمَلَتْهُ أُمُّهُۥ وَهْنًا عَلَىٰ وَهْنٍ وَفِصَٰلُهُۥ فِى عَامَيْنِ أَنِ ٱشْكُرْ لِى
وَلِوَٰلِدَيْكَ إِلَىَّ ٱلْمَصِيرُ ﴿١٤﴾ وَإِن جَٰهَدَاكَ عَلَىٰٓ أَن تُشْرِكَ بِى مَا لَيْسَ لَكَ بِهِۦ عِلْمٌ
فَلَا تُطِعْهُمَا ۖ وَصَاحِبْهُمَا فِى ٱلدُّنْيَا مَعْرُوفًا ۖ وَٱتَّبِعْ سَبِيلَ مَنْ أَنَابَ إِلَىَّ ۚ
ثُمَّ إِلَىَّ مَرْجِعُكُمْ فَأُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿١٥﴾

**14-15.** ሰውንም በወላጆቹ በጎ እንዲያደርግ በጥብቅ አዘዝነው። እናቱ ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው። ጡት መጣያውም በሁለት ዓመት ውስጥ ነው። ለእኔም ለወላጆችህም አመስግን። በማለት አዘዝነው መመለሻው ወደ እኔ ብቻ ነው። ለአንተ በእርሱ እውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢያስገድዱህ አትታዘዛቸው። በቅርቢቱም ዓለም በመልካም ስራ ተወዳጃቸው። ወደ እኔም የተመለሰን ሰው መንገድ ተከተል። ከዚያ መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው። ትሰሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ (አልነው)።

ከሉቅማን ምዕራፍ (15) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ የሸረሪት ምዕራፍ 8 ኛ አንቀፅ ላይ እንዳለፈው ሁሉ በሰዕድ ኢብኑ አቢ ወቃስ እና በእናቱ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ።)

يَٰبُنَيَّ إِنَّهَآ إِن تَكُ مِثۡقَالَ حَبَّةٖ مِّنۡ خَرۡدَلٖ فَتَكُن فِي صَخۡرَةٍ أَوۡ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ أَوۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ يَأۡتِ بِهَا ٱللَّهُۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَطِيفٌ خَبِيرٞ ﴿١٦﴾

**16.** ሉቅማንም አለ ልጄ ሆይ፣ እርሷ (መልካም ተግባር ወይም መጥፎ ተግባር) የሰናፍጭ ቅንጣት ክብደት ያህል እንኳን ብትሆንና በቋጥኝ ውስጥ ወይም በሰማያት ውስጥ ወይም በምድር ውስጥ ብትሆን አላህ ያመጣታል። አላህ ሩህሩህና ውስጠ አዋቂ ነውና።

يَٰبُنَيَّ أَقِمِ ٱلصَّلَوٰةَ وَأۡمُرۡ بِٱلۡمَعۡرُوفِ وَٱنۡهَ عَنِ ٱلۡمُنكَرِ وَٱصۡبِرۡ عَلَىٰ مَآ أَصَابَكَۖ إِنَّ ذَٰلِكَ مِنۡ عَزۡمِ ٱلۡأُمُورِ ﴿١٧﴾ وَلَا تُصَعِّرۡ خَدَّكَ لِلنَّاسِ وَلَا تَمۡشِ فِي ٱلۡأَرۡضِ مَرَحًاۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخۡتَالٖ فَخُورٖ ﴿١٨﴾ وَٱقۡصِدۡ فِي مَشۡيِكَ وَٱغۡضُضۡ مِن صَوۡتِكَۚ إِنَّ أَنكَرَ ٱلۡأَصۡوَٰتِ لَصَوۡتُ ٱلۡحَمِيرِ ﴿١٩﴾

**17-19.** ልጄ ሆይ!ሶላትን አስተካክለህ ስገድ በበጎ ነገርም እዘዝ ከሚጠላም ሁሉ ከልክል በሚያገኝህም መከራ ላይ ታገስ ይህ በምር ከሚያዙ ነገሮች ነው። ጉንጭህንም (በኩራት) ከሰዎች አታዙር። በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሂድ። አላህ ተንበጥራሪን (ኮራተኛ) ጉረኛን ሁሉ አይወድምና። በአካሄድህም መካከለኛ ሁን። ከድምፅህም ዝቅ አድርግ። ከድምፆች ሁሉ አስከፊው የአህዮች ድምጽ ነውና።

**ከሉቅማን ከአንቀፅ (1-19) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቁርአንን ተዓምርነትና የአላህ ጠላቶች መሰሉን ሊፅፉ እንደማይችሉ፤
2. ስለ ሒክማ (ጥበብ) በግልፅ ማስተማር፤
3. ቁርአን ለሰው ልጆች ነፃ አውጪ ስለመሆኑ፤
4. ሰላትና ዘካ ያላቸውን ክብር፤
5. የኢስላም መሰረቶች እምነት፤ ኢስላም ኢህሳን ስለመሆናቸው
6. የሴትን ልጅ ዘፈን መስማት ለባዕድ ወንዶች ክልክል ስለመሆኑ፤
7. የዘፈን ካሴቶችንም ሆነ ሲዲዎች መግዛት ክልክል ስለመሆኑ፤
8. የጭፈራና የዳንስ ስብሰባዎች ላይ መሳተፍ ክልክል ስለመሆኑ፤
9. የኢስላም አስተምህሮት በማግባባት፤ በማበሰርና በማስጠንቀቅ ላይ የተመሰረት ስለመሆኑ፤
10. የአላህ ችሎታ፤ እውቀት ጥበብ ኃያልነት የሚታዩባቸው ኃያል ክንውኖች፤
11. ሰዎች የተሳሳቱትና የጠመሙት ማስረጃ በማጣት ሳይሆን ማስረጃዎችን ጆሮ ዳባ ልበስ በማለት መሆኑን፤
12. ተውሒድን አረጋግጦ ሽርክን ማውገዝ፤
13. ለትልቅም ሆነ ለትንሽ፤ ለዘመድም ሆነ ለባዕድ መምከርና መገሰፅ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
14. ስለ ሽርክ ማክበድና ማስፈራራት፤
15. የጡት መጥቢያ ዘመን ስንት እንደሆነ መግለፅ፤
16. ወላጆችን ማስደሰትና መታዘዝ ተገቢ ስለመሆኑ፤

17. ማንም ሰው ለአላህ ህግ ተፃራሪ ከሆነ በምንም መልኩ ለርሱ መታዘዝ እንደሌለብን፤
18. የአህሉ ሱና ወልጀመዓን መንገድ መከተል ግዴታ ስለመሆኑና የቢድዓ ሰዎችን መንገድ መከተል ክልክል ስለ መሆኑ፤
19. በኢስላም አባትና እናት በልጆቻቸው ላይ ያላቸው መብት ከፍተኛ ሲሆን ያን ከብርና መብት የሚገፉት ኢስላምን የሚፃረር ነገር ሲጠይቁ ብቻ እንደሆነ፤
20. ለአባትና ለእናት ኢስላምን ባይከተሉም በማህበራዊ ህይወታቸው ውስጥ መተባበር በኢስላም ግዴታ መሆኑን፤
21. የአላህን ህግ ማክበርና መልካም ስራ ቢያንስም ቢበዛም ሊናቅ እንደማይገባው፤
22. ሶላትን መስገድ፤ በመልካም ነገር ማዘዝና ከመጥፎ መከልከልና በዚሁም ጉዳይ ላይ ትዕግስት ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ፤
23. የአላህን እውቀት ረቂቅነት፤
24. ትዕግስት በኢስላም ያለውን ከፍተኛ ቦታ፤
25. የማስተማር ተግባር ትዕግስት ካልተጨመረበት በስተቀር ውጤታማ ሊሆን እንደማይችል፤

أَلَمْ تَرَوْاْ أَنَّ ٱللَّهَ سَخَّرَ لَكُم مَّا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلْأَرْضِ وَأَسْبَغَ عَلَيْكُمْ نِعَمَهُۥ ظَٰهِرَةً وَبَاطِنَةًۗ وَمِنَ ٱلنَّاسِ مَن يُجَٰدِلُ فِي ٱللَّهِ بِغَيْرِ عِلْمٍ وَلَا هُدًى وَلَا كِتَٰبٍ مُّنِيرٍ ﴿٢٠﴾ وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱتَّبِعُواْ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ قَالُواْ بَلْ نَتَّبِعُ مَا وَجَدْنَا عَلَيْهِ ءَابَآءَنَآۚ أَوَلَوْ كَانَ ٱلشَّيْطَٰنُ يَدْعُوهُمْ إِلَىٰ عَذَابِ ٱلسَّعِيرِ ﴿٢١﴾

**20-21.** (ሰዎች ሆይ)፣ አላህ በሰማያት እና በምድር ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ለእናንተ የገራላችሁ ፀጋዎችን ግልጽም ይሁኑ ድብቅ የሞላላችሁ መሆኑን አታዩምን? ከሰዎች መካከል ያለ በቂ እውቀትና ያለ መሪ ያለ ግልፅ መጽሀፍም ስለ አላህ የሚከራከር አለ። ለእነርሱም አላህ ያወረደውን ተከተሉ በተባሉ ጊዜ አይደለም በእርሱ ላይ አባቶቻችንን ያገኘንበትን እንከተላለን ይላሉ። ሰይጣን ይህን ተግባር በማስዋብ ወደ እሳት ቅጣት የሚጠራቸው ቢሆንም ይከተሏቸዋልን?።

۞ وَمَن يُسْلِمْ وَجْهَهُۥٓ إِلَى ٱللَّهِ وَهُوَ مُحْسِنٌ فَقَدِ ٱسْتَمْسَكَ بِٱلْعُرْوَةِ ٱلْوُثْقَىٰۗ وَإِلَى ٱللَّهِ عَٰقِبَةُ ٱلْأُمُورِ ﴿٢٢﴾ وَمَن كَفَرَ فَلَا يَحْزُنكَ كُفْرُهُۥٓۚ إِلَيْنَا مَرْجِعُهُمْ فَنُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوٓاْۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿٢٣﴾

**22-23.** እርሱ መልካም ሰሪ ሆኖ ፊቱን ወደ አላህ የሚሰጥ ሰው ሁሉ ጠንካራ ገመድን በእርግጥ ጨበጠ። የነገሩ ሁሉ ፍጻሜ ወደ አላህ ብቻ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ የካደ ሰው ክህደቱ አያሳዝንህ። መመለሻቸው ወደ እኛ ብቻ ነው። የሰሩትንም ሁሉ እንነግራቸዋለን አላህ በልቦች ውስጥ ያለን ሁሉ ያውቃልና።

نُمَتِّعُهُمْ قَلِيلًا ثُمَّ نَضْطَرُّهُمْ إِلَىٰ عَذَابٍ غَلِيظٍ ﴿٢٤﴾ وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۚ قُلِ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٢٥﴾ لِلَّهِ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلْأَرْضِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْغَنِىُّ ٱلْحَمِيدُ ﴿٢٦﴾

**24-26.** ጥቂትን ጊዜ እናጣቅማቸዋለን። ከዚያ ወደ ብርቱ ቅጣት እናስገድዳቸዋለን። ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው ይላሉ። ምስጋና ለአላህ ሁሉ ይገባው በላቸው። ይልቁንም አብዛኞቹ አያውቁም። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነው። አላህ በራሱ ተብቃቂና ምስጉን ነው።

وَلَوْ أَنَّمَا فِى ٱلْأَرْضِ مِن شَجَرَةٍ أَقْلَٰمٌ وَٱلْبَحْرُ يَمُدُّهُۥ مِنۢ بَعْدِهِۦ سَبْعَةُ أَبْحُرٍ مَّا نَفِدَتْ
كَلِمَٰتُ ٱللَّهِ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ حَكِيمٌ ﴿٢٧﴾

**27.** በምድር ያሉ ሁሉ ዛፎች ብዕሮች ቢሆኑ ኖሮ ባህሩም ከእርሱ ማለቅ በኋላ ሰባት ባህሮች የሚጨመሩለት ሆኖ ቀለም ቢሆንና ቢጻፍባቸው የአላህ ቃላት ባላለቀች ነበር። አላህ ሁሉን አሸናፊና ጥበበኛ ነውና።

مَّا خَلْقُكُمْ وَلَا بَعْثُكُمْ إِلَّا كَنَفْسٍ وَٰحِدَةٍ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌۢ بَصِيرٌ ﴿٢٨﴾

**28.** (ሰዎች ሆይ!) እናንተን መፍጠርና እናንተን መቀስቀስ እንደ አንዲት ነፍስ እንጂ ሌላ አይደለም። አላህ ሰሚና ተመልካች ነውና።

**ከሉቅማን ምዕራፍ ከአንቀፅ (20-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ፍጡሩን አይቶ የፈጣሪን መኖር ማረጋገጥ፤
2. የአላህን ፀጋዎች ማወቅና ማመስገን ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. ያለ እውቀት መከራከር ክልክል ስለመሆኑ፤
4. በመጥፎ ነገር ላይ ሌላን ተከትሎ መጓዝ ክልክል ስለመሆኑ
5. የላኢላሀ ኢለሏህ ሰዎች ትክክለኛ ነፃ ሰዎች መሆናቸውን፤
6. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
7. የአረብ አጋሪዎች በአላህ ጌትነት አንድነት ላይ ሽርክ እንዳልነበራቸው ነገር ግን ከአላህ ጋር ሌላን በማምለክ በአምልኮ አጋሪዎች እንደነበሩ፤
8. የአላህ እውቀት ሰፊ ስለመሆኑ፤
9. የሰዎች እውቀት በአላህ እውቀት አንፃር ምንም እንዳልሆነ፤
10. የአላህ ችሎታ በምንም የማይገደብና ምንም የማይሳነው መሆኑን፤
11. ከአላህ ባህሪያት ጥቂቶቹን አልፎ አልፎ መጥቀሱን እንማራለን።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يُولِجُ ٱلَّيْلَ فِى ٱلنَّهَارِ وَيُولِجُ ٱلنَّهَارَ فِى ٱلَّيْلِ وَسَخَّرَ ٱلشَّمْسَ وَٱلْقَمَرَ
كُلٌّ يَجْرِىٓ إِلَىٰٓ أَجَلٍ مُّسَمًّى وَأَنَّ ٱللَّهَ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ٢٩ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْحَقُّ
وَأَنَّ مَا يَدْعُونَ مِن دُونِهِ ٱلْبَٰطِلُ وَأَنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْعَلِىُّ ٱلْكَبِيرُ ٣٠

**29-30.** (የሰው ልጅ ሆይ)፣ አላህ ሌሊትን በቀን ውስጥ የሚያስገባ ቀንንም በሌሊት ውስጥ የሚያስገባ ፀሀይንና ጨረቃንም የገራ መሆኑን አታይምን? ሁሉም እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ይሮጣሉ። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው። ይህም አላህ ብቸኛ አምላክነት እውነት በመሆኑ፤ ከእርሱ ሌላ የሚገዙት ጣዖት ሁሉ ውሸት በመሆኑና አላህ የበላይ ታላቅ በመሆኑ ብቻ ነው።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱلْفُلْكَ تَجْرِى فِى ٱلْبَحْرِ بِنِعْمَتِ ٱللَّهِ لِيُرِيَكُم مِّنْ ءَايَٰتِهِۦٓ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ
لِّكُلِّ صَبَّارٍ شَكُورٍ ٣١ وَإِذَا غَشِيَهُم مَّوْجٌ كَٱلظُّلَلِ دَعَوُا۟ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ فَلَمَّا
نَجَّىٰهُمْ إِلَى ٱلْبَرِّ فَمِنْهُم مُّقْتَصِدٌ وَمَا يَجْحَدُ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَّا كُلُّ خَتَّارٍ كَفُورٍ ٣٢

**31-32.** (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ሊያሳያችሁ መርከቦች በአላህ ችሎታ በባህር ውስጥ የሚንሻለሉ መሆናቸውን አታይምን? በዚህ ውስጥ በጣም ታጋሽ አመስጋኝ ለሆኑ ሁሉ ተአምራቶች አሉበት። እንደ ጥላዎች የሆነ ማዕበል በሸፈናቸው ጊዜ ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ ያጠሩ ሆነው አላህን ይጠሩታል። ወደ የብስ ባዳንናቸው ጊዜ ግን ከእነርሱ መካከል ትክክለኛም አለ ከእነርሱም የሚክድ አለ። በአንቀፆቻችንም አታላይና ከዳተኛ የሆነ ሁሉ እንጂ ሌላው አይክድም።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱتَّقُوا۟ رَبَّكُمْ وَٱخْشَوْا۟ يَوْمًا لَّا يَجْزِى وَالِدٌ عَن وَلَدِهِۦ وَلَا مَوْلُودٌ هُوَ جَازٍ عَن
وَالِدِهِۦ شَيْـًٔا إِنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّ فَلَا تَغُرَّنَّكُمُ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا وَلَا يَغُرَّنَّكُم بِٱللَّهِ ٱلْغَرُورُ ٣٣

**33.** እናንተ ሰዎች ሆይ! ጌታችሁን ፍሩ። ወላጅ ከልጁ በምንም የማይጠቅምበት ልጅም እርሱ ወላጅን በምንም ጠቃሚ የማይሆንበትን ቀን ፍሩ። የአላህ ቀጠሮ እውነት ነውና። ቅርቢቱም ህይወት አትሸምግላችሁ። በአላህ ከመታገስ አታላዩ ሰይጣን አያታልላችሁ።

إِنَّ ٱللَّهَ عِندَهُۥ عِلۡمُ ٱلسَّاعَةِ وَيُنَزِّلُ ٱلۡغَيۡثَ وَيَعۡلَمُ مَا فِي ٱلۡأَرۡحَامِۖ وَمَا تَدۡرِي نَفۡسٞ مَّاذَا تَكۡسِبُ غَدٗاۖ وَمَا تَدۡرِي نَفۡسُۢ بِأَيِّ أَرۡضٖ تَمُوتُۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرُۢ ٣٤

**34.** አላህ የሰዓቲቱ እውቀት እርሱ ዘንድ ብቻ ነው። ዝናብንም ያወርዳል። በማህፀኖችም ውስጥ ያለን ሁሉ ያውቃል ማንኛይቱም ነፍስ ነገ የምትሰራውን አታውቅም። ማንኛይቱም ነፍስ በየትኛው ምድር እንደምትሞት አታውቅም። አላህ አዋቂና ውስጠ አዋቂ ነው።

**ከሉቅማን ምዕራፍ ከአንቀፅ (29-34) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ተውሒድን አፅድቆ ሽርክን ማውገዝ፣
2. ታጋሽነትና አላህን ማመስገን ተገቢ ስለመሆኑ፣
3. አጋሪዎች ቁርኣን በሚወርድበት ጊዜ በችግር ዘመን አላህን አንድ ያደርጉት እንደነበርና በደስታ ጊዜ ደግሞ እንደሚያሻርኩ፣
4. የሶላትንና የተቅዋን አስፈላጊነት፣
5. ስለ ሙቶ መነሳት ሀቅነት፣
6. በዚህች ዓለም ደስታ ከመታለል ማስጠንቀቅ፣
7. አምስቱን የገይብ ነገሮች ምን ምን እንደሆኑ ማስታወስ፣
8. ገይብ አውቃለሁ የሚል ሁሉ ጣኦታዊ እንደሆነ፣
9. አላህ «በማህጸኖችም ውስጥ ያለን ነገር ሁሉ ያውቃል። ከእሱም ውጭ ማህፀን ምን እንደቋጠረች የሚያውቅ የለም»ይህ አባባል የሚያሳየው ዘር ወደ ማህፀን ገብቶ ሲቋጠር ጀምሮ ባለው ሂደት በትክክል መፀነሱን፣ ፆታውን፣ መልኩን... ወዘተ ከአላህ በስተቀር የሚያውቀው የለም ማለት ሲሆን በአሁኑ ዘመን በመሳሪያ ታግዘው በሴቶች ማህፀን ውስጥ ያለ ፅንስ ሁኔታ እናውቃለን የሚሉት ጠበብቶች ሆዷን አልፎ በሚያሳይ መሳሪያ ታግዘው እንጂ አላህ አታውቁትም ያለውን ሚስጥር ደርሰውበት እንዳልሆነ ሊታወቅ እንደሚገባ፣
10. ይህን ዓለም በትክክል ያጤነ የአላህን ብቸኛ አምላክነት እንደሚያረጋግጥ፣
11. ሰዎች አላህን እንዲፈሩ የትንሳኤን ቀንን እንዲያስታውሱ ማዘዝ።
12. በማህፀን ያለውን አታውቁም ማለት ሴት ወይም ወንድ መሆኑን ብቻ ማለት ሳይሆን እድሜውን፣ ስራውን፣ መልኩን ወዘተ. የሚለውን ሁሉ እንደሚያጠቃልል እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የሉቅማን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (32)
# የስግደት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሰጅዳህ)

سُورَةُ السَّجْدَةِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (30) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

الٓمٓ ١

**1.** አሊፍ፤ ላም፤ ሚይም፤*

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

تَنزِيلُ ٱلۡكِتَٰبِ لَا رَيۡبَ فِيهِ مِن رَّبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٢ أَمۡ يَقُولُونَ ٱفۡتَرَىٰهُۚ بَلۡ هُوَ ٱلۡحَقُّ مِن
رَّبِّكَ لِتُنذِرَ قَوۡمٗا مَّآ أَتَىٰهُم مِّن نَّذِيرٖ مِّن قَبۡلِكَ لَعَلَّهُمۡ يَهۡتَدُونَ ٣

**2-3.** የመጽሐፉ መወረድ ጥርጥር የለበትም። የወረደውም ከዓለማት ጌታ ነው። ቀጠፈው ይላሉን? አይደለም እርሱ እውነት ነው። በእርሱ ከአንተ በፊት ከአስፈራሪ ነቢይ ያልመጣባቸውን ሕዝቦች እርሱ ልታስፈራራበት ያወረደልህ ነው። እነርሱ ሊመሩ ይከጀላልና።

ٱللَّهُ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَا فِي سِتَّةِ أَيَّامٖ ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ
مَا لَكُم مِّن دُونِهِۦ مِن وَلِيّٖ وَلَا شَفِيعٍۚ أَفَلَا تَتَذَكَّرُونَ ٤ يُدَبِّرُ ٱلۡأَمۡرَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ إِلَى
ٱلۡأَرۡضِ ثُمَّ يَعۡرُجُ إِلَيۡهِ فِي يَوۡمٖ كَانَ مِقۡدَارُهُۥٓ أَلۡفَ سَنَةٖ مِّمَّا تَعُدُّونَ ٥
ذَٰلِكَ عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ ٱلۡعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ٦

**4-6.** አላህ ያ፣ ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውን ሁሉ በስድስት ቀኖች ውስጥ የፈጠረ ከዚያ በዐርሹ ላይ ከፍ አለ። ከእርሱ ሌላ ለእናንተ

ወዳጅም አማላጅም ምንም የላችሁም። አትገሰፁምን? ነገሩን ሁሉ ከሰማይ ወደ ምድር ያዘጋጃል፤ ከዚያ ከምትቆጥሩት (ዘመን) ልኩ ሺህ ዓመት በሆነ ቀን ውስጥ ወደ እርሱ ይወጣል። ይህንን ያደረገ አላህ ሩቅንም ቅርቡንም ሁሉ አዋቂው፣ አሸናፊ፤ አዛኝ ጌታ ነው።

ٱلَّذِىٓ أَحْسَنَ كُلَّ شَىْءٍ خَلَقَهُۥ ۖ وَبَدَأَ خَلْقَ ٱلْإِنسَٰنِ مِن طِينٍ ﴿٧﴾
ثُمَّ جَعَلَ نَسْلَهُۥ مِن سُلَٰلَةٍ مِّن مَّآءٍ مَّهِينٍ ﴿٨﴾ ثُمَّ سَوَّىٰهُ وَنَفَخَ فِيهِ مِن رُّوحِهِۦ ۖ
وَجَعَلَ لَكُمُ ٱلسَّمْعَ وَٱلْأَبْصَٰرَ وَٱلْأَفْـِٔدَةَ ۚ قَلِيلًا مَّا تَشْكُرُونَ ﴿٩﴾

**7-9.** ያ፣ የፈጠረውን ነገር ሁሉ ያሳመረው። የሰውንም ፍጥረት ከጭቃ የጀመረው ነው። ከዚያ ዘሮቹን ከተንጣለለ ከደካማ ውሃ ያደረገ ነው። ከዚያ ቅርፁን አስተካከለው በእርሱ ውስጥም ከመንፈሱ ነፍስ ዘራበት። ለናንተም ጆሮዎችን ዓይኖችንና ልቦችንም አደረገላችሁ በጣም ጥቂትን ብቻ ታመሰግናላችሁ።

وَقَالُوٓا۟ أَءِذَا ضَلَلْنَا فِى ٱلْأَرْضِ أَءِنَّا لَفِى خَلْقٍ جَدِيدٍۭ ۚ
بَلْ هُم بِلِقَآءِ رَبِّهِمْ كَٰفِرُونَ ﴿١٠﴾ ۞ قُلْ يَتَوَفَّىٰكُم مَّلَكُ ٱلْمَوْتِ ٱلَّذِى وُكِّلَ بِكُمْ
ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُمْ تُرْجَعُونَ ﴿١١﴾ وَلَوْ تَرَىٰٓ إِذِ ٱلْمُجْرِمُونَ نَاكِسُوا۟ رُءُوسِهِمْ عِندَ رَبِّهِمْ
رَبَّنَآ أَبْصَرْنَا وَسَمِعْنَا فَٱرْجِعْنَا نَعْمَلْ صَٰلِحًا إِنَّا مُوقِنُونَ ﴿١٢﴾
وَلَوْ شِئْنَا لَءَاتَيْنَا كُلَّ نَفْسٍ هُدَىٰهَا وَلَٰكِنْ حَقَّ ٱلْقَوْلُ مِنِّى لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنَ ٱلْجِنَّةِ
وَٱلنَّاسِ أَجْمَعِينَ ﴿١٣﴾ فَذُوقُوا۟ بِمَا نَسِيتُمْ لِقَآءَ يَوْمِكُمْ هَٰذَآ إِنَّا نَسِينَٰكُمْ ۖ
وَذُوقُوا۟ عَذَابَ ٱلْخُلْدِ بِمَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿١٤﴾

**10-14.** በምድርም ውስጥ በስብሰን በጠፋን ጊዜ እኛ በአዲስ መፈጠር ውስጥ እንሆናለን? አሉ። በእውነቱ እነርሱ በጌታቸው መገናኘት ከሓዲያን ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእናንተ የተወከለው መልአከ ሞት ይገድላችኋል። ከዚያ ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ በላቸው። አመፀኞች በጌታቸው ዘንድ ራሶቻቸውን ያቀረቀሩ ሆነው:- ጌታችን ሆይ፣ አየን ሰማንም መልካምን እንሠራለንና ወደ ምድረ ዓለም መመልሰን እኛ አረጋጋጮች ነን

የሚሉ ሲሆኑ ብታይ ኖሮ (አስደንጋጭን ነገር ይታይ ነበር)። በሻንም ኖሮ ነፍስን ሁሉ ቅንነቷን በሰጠናት ነበር። ግን ገሀነምን ከአጋንንትና ከሰዎች የተሰበሰቡ ሆነው በእርግጥ እሞላለሁ ማለት ቃሉ ከእኔ ተረጋግጧል። ይህንንም ቀናችሁን መገናኘትን በመርሳታችሁ ምክንያት ቅጣትን ቅመሱ! እኛ ተውናችሁ ትሰሩት በነበራችሁትም ጥፋት ዘውታሪን ቅጣት ቅመሱ ይባላሉ።

إِنَّمَا يُؤْمِنُ بِـَٔايَٰتِنَا ٱلَّذِينَ إِذَا ذُكِّرُواْ بِهَا خَرُّواْ سُجَّدًا وَسَبَّحُواْ بِحَمْدِ رَبِّهِمْ وَهُمْ لَا يَسْتَكْبِرُونَ ۩ ﴿١٥﴾ تَتَجَافَىٰ جُنُوبُهُمْ عَنِ ٱلْمَضَاجِعِ يَدْعُونَ رَبَّهُمْ خَوْفًا وَطَمَعًا وَمِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿١٦﴾

**15-16.** በአንቀፆቻችን የሚያምኑት እነዚያ በእርሷ በተገሰፁ ጊዜ ሰጋጆች ሆነው የሚወድቁትና እነርሱም የማይኮሩ ሆነው በጌታቸው ምስጋና (ተጎናፅፈው)። የሚያወድሱት ሰዎች ብቻ ናቸው። ጌታቸውን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ቦታዎቻቸው ይርቃሉ ከሰጠናቸውም ፀጋ* ይለግሳሉ።

✷ ከ (15-17) ያሉትን የነዚህን አናቅፅ በተመለከተ የተፍሲር ምሁራን ብዙ ሐዲሶች ተዘግበዋል። ከነዚህ መካከል አቡ ዳውድና ቲርሚዝይ በዘገቡት ሐዲስ ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «የመልካም ነገሮችን መግቢያ በሮች ላመላክታችሁን? እነርሱም ፆም ከጀሀነም መከላከያ ጋሻ ነው። ውሃ እሳትን እንደሚያጠፋ ሁሉ ሰደቃ ኃጢአቶችን ያጠፋል። አንድ ሰው በሌሊት የሚሰግደው ሶላት ነው» ካሉ በኋላ «ጌታችሁን ለመፍራትና ለመከጀል የሚጠሩት ሆነው ጎኖቻቸው ከመጋደሚያ ስፍራዎች ያርቃሉ፤ ከሰጠናቸውም ፀጋ ይለግሳሉ» (የስግደት ምእራፍ፡ 16) የሚለውን አንቀፅ አነበቡ።»

فَلَا تَعْلَمُ نَفْسٌ مَّآ أُخْفِىَ لَهُم مِّن قُرَّةِ أَعْيُنٍ جَزَآءًۢ بِمَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿١٧﴾

**17.** ይሰሩት በነበሩት ለመመንዳት ከዓይኖች መርጊያ ለእነርሱ የተደበቀላቸውን ፀጋ ማንኛይቱም ነፍስ አታውቅም።*

✷ ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ጀነት የሚያስገባኝና ከእሳት የሚያርቀኝን በጎ ስራ ይንገሩኝ?» አልኳቸው። «ትልቅ ነገር ጠይቀሃል። አላህ ላገራለት ሰው በእርግጥ ገርና ቀላል ነው። አላህን በርሱ ላይ ምንም አካል ሳታጋራ አምልክ። ሶላትን ደንበውን ጠብቀህ ስገድ። ዘካ ስጥ። ረመዷንን ፁም። የአላህን ቤት ወደርሱ የመሄድ አቅም ካለህ ሐጅ አድርግ» ካሉ በኋላ «የደግ ስራን በሮች ላመላክትህን? ፆም ጋሻ ነው። እሳት ውሃን እንደሚያጠፋው ምፅዋት ኃጢአትን ታጠፋለች። ሰውየው በሌሊት መሀል የሚሰግደውም ሶላት ተጠቃሽ ነው» አሉና፦ «ጎናችሁ ከመኝታዎች ይራራቃሉ» አስ. ሰጅዳህ

(16-17) የሚለውን የቁርኣን አንቀፅ «ይሰራሉ» እስከሚለው ድረስ አነበቡ» ከዚያም «የነገሮችን ሁሉ ራስ ዋና ምሰሶውንና ጉልላቱን ልንገርህ?» ሲሉ ጠየቁኝ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አዎ ይንገሩን» አልኳቸው። «የነገሮች ሁሉ ዋና ኢስላም ነው። ምሰሶው ሶላት ነው። ጉልላቱ በአላህ መንገድ የሚደረግ ትግል ነው» አሉኝ። ከዚያም «የዚህን ሁሉ ተግባር መቋጠሪያ ውል ልንገርህን?» አሉኝ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አዎ ይንገሩኝ» አልኳቸው። ምላሳቸውን ያዙና፦ «ይህችን ጠብቅ» አሉኝ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በምንናገረው እንጠየቃለን?» አልኳቸው። «እናትህ ትጣህ፤ ሰዎች እሳት ውስጥ በፊቶቻቸው የሚገቡት በምላሶቻቸው ውጤት ምክንያት አይደለምን?» አሉ።

أَفَمَن كَانَ مُؤۡمِنٗا كَمَن كَانَ فَاسِقٗاۚ لَّا يَسۡتَوُۥنَ ١٨
أَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَلَهُمۡ جَنَّٰتُ ٱلۡمَأۡوَىٰ نُزُلَۢا بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٩
وَأَمَّا ٱلَّذِينَ فَسَقُواْ فَمَأۡوَىٰهُمُ ٱلنَّارُۖ كُلَّمَآ أَرَادُوٓاْ أَن يَخۡرُجُواْ مِنۡهَآ أُعِيدُواْ فِيهَا
وَقِيلَ لَهُمۡ ذُوقُواْ عَذَابَ ٱلنَّارِ ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ٢٠
وَلَنُذِيقَنَّهُم مِّنَ ٱلۡعَذَابِ ٱلۡأَدۡنَىٰ دُونَ ٱلۡعَذَابِ ٱلۡأَكۡبَرِ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ٢١
وَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّن ذُكِّرَ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِۦ ثُمَّ أَعۡرَضَ عَنۡهَآۚ إِنَّا مِنَ ٱلۡمُجۡرِمِينَ مُنتَقِمُونَ ٢٢

**18-22.** አማኝ የሆነ ሰው አመፀኛ እንደሆነ ሰው ነውን? አይስተካከሉም። እነዚያ ያመኑና መልካሞችን የሰሩማ ለነሱ ይሰሩ በነበሩት ምክንያት መስተንግዶ ሲሆኑ መኖሪያ ገነቶች አሏቸው። እነዚያ ያመፁትማ መኖሪያቸው እሳት ናት። ከእርሷ መውጣትን በፈለጉ ቁጥር በእርሷ ውስጥ ይመለሳሉ ለእነርሱም ያንን በእርሱ ታስተባብሉበት የነበራችሁትን የእሳት ቅጣት ቅመሱ ይባላሉ። ይመለሱ ዘንድ ከትልቁ ቅጣት በፊት በዚህ ዓለም ትንሹን ቅጣት በእርግጥ እናቀምሳቸዋለን። በጌታውም አንቀፆች ከተገሰፀና ከዚያ ከተዋተ ሰው ይበልጥ በደለኛ ማነው? (የለም) እኛ ከተንኮለኞቹ ተበቃዮች ነን።

ከስግደት ምዕራፍ (18-22) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ እነዚህ አናቅፅ የወረዱት ወሊድ ኢብኑ ዑቅባህ ለዓሊይ «እኔ ከአንተ የተሻለ ምላስ አለኝ፤ ጦሬም ከአንተ ይሻላል፤ በሰውትም የተሻልኩኝ ነኝ» አለው። «ዓሊይም ዝምበል አንተ እኮ ፋሲቅ ነህ» ስላለው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ فَلَا تَكُن فِى مِرْيَةٍ مِّن لِّقَآئِهِۦ ۖ وَجَعَلْنَٰهُ هُدًى لِّبَنِىٓ
إِسْرَٰٓءِيلَ ﴿٢٣﴾ وَجَعَلْنَا مِنْهُمْ أَئِمَّةً يَهْدُونَ بِأَمْرِنَا لَمَّا صَبَرُوا۟ ۖ وَكَانُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا يُوقِنُونَ ﴿٢٤﴾
إِنَّ رَبَّكَ هُوَ يَفْصِلُ بَيْنَهُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ فِيمَا كَانُوا۟ فِيهِ يَخْتَلِفُونَ ﴿٢٥﴾

**23-25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳን መጽሐፍን በእርግጥ ሰጠነው። እርሱን ከመገናኘትህም በመጠራጠር ውስጥ አትሁን። ለኢስራኤል ልጆችም መሪ አደረግነው። በታገሱና በተዐምራቶቻችን የሚያረጋግጡ በሆኑም ጊዜ ከነርሱ በትዕዛዛችን የሚመሩ መሪዎችን አደረግን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ በዚያ ይለያዩበት በነበሩት ነገር በትንሳዔ ቀን በመካከላቸው በፍርድ ይለያል።

أَوَلَمْ يَهْدِ لَهُمْ كَمْ أَهْلَكْنَا مِن قَبْلِهِم مِّنَ ٱلْقُرُونِ يَمْشُونَ فِى مَسَٰكِنِهِمْ ۚ
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ ۖ أَفَلَا يَسْمَعُونَ ﴿٢٦﴾

**26.** ከክፍለ ዘመናት ሰዎች ብዙዎችን ያጠፋን መሆናችን በመኖሪያዎቻቸው የሚሄዱ ሲሆኑ ለእነርሱ አልተገለፀላቸውምን? በዚህ ውስጥ ምልክቶች አሉበት አይሰሙምን?

أَوَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّا نَسُوقُ ٱلْمَآءَ إِلَى ٱلْأَرْضِ ٱلْجُرُزِ فَنُخْرِجُ بِهِۦ زَرْعًا تَأْكُلُ مِنْهُ أَنْعَٰمُهُمْ
وَأَنفُسُهُمْ ۖ أَفَلَا يُبْصِرُونَ ﴿٢٧﴾

**27.** እኛ ውሃን ወደ ደረቅ ምድር የምንነዳ እንስሶቻቸውና ነፍሶቻቸው ከርሱ የሚበሉለትንም አዝመራ በእርሱ የምናወጣ መሆናችንን አያዩምን? አይመለከቱምን?

وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلْفَتْحُ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٢٨﴾ قُلْ يَوْمَ ٱلْفَتْحِ لَا يَنفَعُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟
إِيمَٰنُهُمْ وَلَا هُمْ يُنظَرُونَ ﴿٢٩﴾ فَأَعْرِضْ عَنْهُمْ وَٱنتَظِرْ إِنَّهُم مُّنتَظِرُونَ ﴿٣٠﴾

**28-30.** ከእውነተኞችም እንደ ሆናችሁ ይህ ፍርድ መቼ ነው? ይላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በፍርዱ ቀን* እነዚያን የካዱትን ሰዎች እምነታቸው አይጠቅማቸውም። እነርሱም ጊዜን አይሰጡም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱን ተዋቸው። ተጠባበቅም። እነርሱም ተጠባባቂዎች ናቸውና።

✷ ይህ ቀን የትኛው ቀን እንደሆነ ማለትም «የትንሳኤ ዕለት» ወይም «የበድር ቀን» ወይም «የመካ መከፈት» ማለት ሊሆን እንደሚችል የተፍሲር ባለሙያወች የተከራከሩበት ቢሆንም የተመረጠው ግን «የፍርድ ቀን» ማለቱ ሲሆን ያ የፍርድ ቀን የትንሳኤ ዕለትም ሆነ የበድር ቀን ሊሆን ይችላል የሚለው ነው። በመካ መከፈት ሊሆን ይችላል ያለው ግን ተቀባይነት የለውም። የመካ መከፈት ዕለት ከሓዲያን በእምነታቸው አይጠቅማቸውም» ማለት አይቻልምና።

በአላህ የስግደት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (33)
# የአህዛቦች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልአህዛብ)

سُورَةُ الأَحْزَابِ

### በመዲና ወረደ። የምእራፉ አናቅፅ በሁሉም ዘንድ (73) ናቸው።
### የሱረቱ አል አህዛብ መግቢያ

ነብዩን አላህን እንዲፈሩ፤ በሱ ላይ እንዲመኩ በመምከር ስለ መቃብር፤ ስለ ልጅ በማድረግ የሚያስጠጓቸውን ልጆች አያያዝ ህግና ስርዓት ከጃሂሊያው መርሆ አውጥቶ ኢስላማዊ ህግ አልብሷል አባቶቻቸውም የወለዷቸው እንጂ ያሳደገችው እንዳልሆኑ፤ አላህ ለነብዩ (ﷺ) የቸራቸውን ክብር፤ ለባለቤቶቻቸውም ሊሰጣቸው የሚገባውን ክብር አላህ ለነብያት አደራ ያለውን ኃላፊነት፤ በአህዛብ ዘመቻ ዕለት የነበረው ስጋትና ጭንቀት፤ ሙዕሚኖች ያጋጠማቸውን ድል፤ የነብዩ (ﷺ) ሚስቶች ሊኖራቸው የሚገባውን ስርዓት፤ ነብዩ (ﷺ) በአስተማሪነታቸው ያሳዩትን መልካም አርአያ፤ ለነብዩ (ﷺ) ብቻ እነሱ ራሳቸው ራሳችንን ሰጠን ለሚሉ ሴቶች ምን እንደሚፈቀድና ለነብዩ ከዘጠኝ በላይ ማግባት እንደማይፈቀድላቸው በዝርዝር ያስረዳል። በማስከተልም ሙስሊሞች ወደ ነብዩ ቤት ሲገቡና ከእርሳቸው ቤት ሲወጡ ሊያሟሏቸው የሚገቡ ስርዓችን፤ የእሳቸውን ሚስቶች አንድ ነገር ለመጠየቅ የፈለገ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበትም አንድ በአንድ ያስተምራል።

የነብዩ (ﷺ) ሚስቶችን አለባበስ እንኳን ሳይቀር በግልፅ ያስረዳል። ስለ ትንሳኤ ዕለትና ስለ ምልክቶቹ ያወሳና አላህን ስለ መፍራት ይመክራል።

በስተመጨረሻም የሰው ልጅ የተሸከመውና የጣለባት ኃላፊነት ሰማያትና ምድር እንዲሁም ጋራዎች ለመሸከም አንችልም ያሉትና የሰው ልጅ ግን ራሱን በዳይ ሆኖ እወጣዋለሁ በማለት ኃላፊነቱን የተቀበለ መሆኑን በማውሳት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

ነብዩ (ﷺ) ለመልካም ነገር አሳቢዎች ሁሉ ብቸኛ አርአያ ናቸውም በ ውስጥ ተወስቷል። እሳቸውን አርአያ ያደረገ ሁሉ መቼም አይሳሳትም። ለተግባሩም ዋስትና አለው። በሶላቱ፤ በፆሙ፤ በሐጁ፤ በአስተምህሮት፤ በመልካም ስነ ምግባራት ሁሉ መልካም አርአያ ናቸው። እራሳቸውም ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ፦ «እኔ ስሰግድ እንዳያችሁ ሁሉ ስገዱ» ብለዋል። ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ፦ «አላህ በጀመረበት ነገር ጀምሩ» «የሐጅ ፀሎታችሁን ከኔ ውሰዱ» ብለዋል። ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ከእሱንና የሸሸ ሰው የእኔ አባል አይደለም» በማለት ለሁሉም ነገር እሳቸውን አርአያ ማድረግ አማራጭ የሌለው መሆኑን አስተምረዋል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ ٱتَّقِ ٱللَّهَ وَلَا تُطِعِ ٱلۡكَٰفِرِينَ وَٱلۡمُنَٰفِقِينَۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمًا ١

**1.** አንተ ነብይ ሆይ! አላህን ፍራ። ከሓዲያንንና መናፍቃንን አትታዘዝ። አላህ አዋቂ፤ ጥበበኛ ነውና።

وَٱتَّبِعۡ مَا يُوحَىٰٓ إِلَيۡكَ مِن رَّبِّكَۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٗا ٢
وَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَكِيلٗا ٣

**2-3.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከጌታህ ወደ አንተ የሚወረደውን ብቻ ተከተል። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ላይ ተመካ። መመኪያነት በአላህ ብቻ በቃ።

ከአህዛቦች ምዕራፍ ከ (1-3) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የመካ ሰዎች ወደ ነብዩ መጥተው «አቋምህን ከቀየርክ ግማሽ ንብረታችንን እንሰጥሀለን» ስላሏቸውና አስመሳዮችና አይሁዶች «ሀሳብህን ካልቀየርክ ለሕይወትህ ያሰጋሀል» ይሏቸው ስለነበረ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት።

مَّا جَعَلَ ٱللَّهُ لِرَجُلٖ مِّن قَلۡبَيۡنِ فِي جَوۡفِهِۦۚ وَمَا جَعَلَ أَزۡوَٰجَكُمُ ٱلَّٰٓـِٔي تُظَٰهِرُونَ مِنۡهُنَّ
أُمَّهَٰتِكُمۡۚ وَمَا جَعَلَ أَدۡعِيَآءَكُمۡ أَبۡنَآءَكُمۡۚ ذَٰلِكُمۡ قَوۡلُكُم بِأَفۡوَٰهِكُمۡۖ وَٱللَّهُ يَقُولُ ٱلۡحَقَّ
وَهُوَ يَهۡدِي ٱلسَّبِيلَ ٤ ٱدۡعُوهُمۡ لِأٓبَآئِهِمۡ هُوَ أَقۡسَطُ عِندَ ٱللَّهِۚ فَإِن لَّمۡ تَعۡلَمُوٓاْ ءَابَآءَهُمۡ
فَإِخۡوَٰنُكُمۡ فِي ٱلدِّينِ وَمَوَٰلِيكُمۡۚ وَلَيۡسَ عَلَيۡكُمۡ جُنَاحٞ فِيمَآ أَخۡطَأۡتُم بِهِۦ وَلَٰكِن مَّا
تَعَمَّدَتۡ قُلُوبُكُمۡۚ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورٗا رَّحِيمًا ٥

**4-5.** (ሙስሊሞች ሆይ!) አላህ ለአንድ ሰው በሆዱ ውስጥ ሁለትን ልቦች አላደረገም። እነዚያን እንደናቶቻችን ጀርባዎች ይሁኑብን የምትሏቸውን ሚስቶቻችሁንም እናቶቻችሁ አላደረገም። ልጅ በማድረግ የምታስጠጓቸውን ልጆቻችሁ አላደረገም። ይህ በአፎቻችሁ የምትሉት ብቻ ነው። አላህ እውነትን ይናገራል። እርሱም ትክክለኛውን መንገድም ይመራል። (ሙስሊሞች ሆይ!) ልጅ በማድረግ የምታስጠጓቸውን በአባቶቻቸው ስም በማስጠጋት ጥሯቸው። እርሱ አላህ ዘንድ ትክክለኛው መንገድ ነውና።

አባቶቻቸውን ባታውቁ በሃይማኖት ወንድሞቻችሁና ዘመዶቻችሁ ናቸው። በእርሱ በተሳሳታችሁበት ነገርም በእናንተ ላይ ኃጢአት የለባችሁም። ግን ልቦቻችሁ አውቀው በሰራችሁት ስህተት ኃጢአት አለባችሁ። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

ከአህዛቦች ምዕራፍ (4) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ጀሚል ኢብኑ መዕመር የተባለ የሰማውን ሁሉ የማይረሳ ሰው ነበር። ይህ ሰው «እኔ ሁለት ልብ አለኝ ስለዚህ ከሙሐመድ የበለጠ ማሰብ እችላለሁ» ይል ነበር። የበድር ቀን እያሉ መኮች ተሸንፈው ሲሸሹ ይህ ሰው እየሸሸ ነበር። አንዱን ጫማውን በእጁ ሌላውን በእግሩ አድርጎ ሲሮጥ አቡ ሱፍያን አየውና «ምነው ጫማህን አንዱን በእጅህ ሌላውን በእግርህ አደረከው ሲለው» ወይም ሁለቱም በእግሬ ያሉ መስሎኝ ነበር» አለው። በዚህ ጊዜ «ባለሁለት ልብ ነኝ» ይል የነበረ ሁሉ ውሸት መሆኑን ተረጋገጠ።

(ለ) አንዳንድ አስመሳዮች ነብዩን «ሁለት ልብ ነው ያላቸው ምክንያቱም በአንድ ጉዳይ ላይ ሆነው ሌላ ይሰራሉ። ከዚያም ወደ ፊተኛው ስራ ሲመለሱ ምንም ስህተት አይፈፅሙም» ይሉ ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

ٱلنَّبِيُّ أَوۡلَىٰ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ مِنۡ أَنفُسِهِمۡۖ وَأَزۡوَٰجُهُۥٓ أُمَّهَٰتُهُمۡۗ وَأُوْلُواْ ٱلۡأَرۡحَامِ بَعۡضُهُمۡ أَوۡلَىٰ بِبَعۡضٖ فِي كِتَٰبِ ٱللَّهِ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُهَٰجِرِينَ إِلَّآ أَن تَفۡعَلُوٓاْ إِلَىٰٓ أَوۡلِيَآئِكُم مَّعۡرُوفٗاۚ كَانَ ذَٰلِكَ فِي ٱلۡكِتَٰبِ مَسۡطُورٗا ٦

6. ነብዩ ሙሐመድ ምእመናን ከነፍሶቻቸው* ይበልጥ ቀራቢ ነው። ሚስቶቹም እናቶቻቸው ናቸው። የዝምድና ባለቤቶች ከፊላቸው በከፊሉ ላይ (ለውርስ) በአላህ መጽሐፍ ውስጥ ከአማኞችና ከስደተኞች ይልቅ የተገባቸው ናቸው። ለወዳጆቻችሁ በኑዛዜ መልካም ስራን ብትሰሩ ግን ይፈቀዳል። ይህ በአላህ መጽሐፉ ውስጥ ቀድሞውኑ የተመዘገበ ነው።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ ኢብኑ ሂሻም እንዳስተላለፉት በአንድ ወቅት ከአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጋር አብረን ሳለን እሳቸው የዑመር ኢብኑ አልኸጣኢብኑ እጅ ይዘው ነበር። ዑመር «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! እርሶ በእኔ ዘንድ ከማንም በላይ የተወደዱ ኖት። ከነፍሴ በስተቀር» አሏቸው። እሳቸውም «ነፍሱ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ! እኔ ካንተ ዘንድ ከነፍስህ በላይ የተወደድኩ እስካልሆንኩኝ ድረስ በእርግጥ እምነትህ ሙሉ አይደለም» አሏቸው። ዑመርም «በአላህ እምላለሁ! እርስዎ በኔ ዘንድ ከነፍሴ ይበልጥ የተወደዱ ነዎት» አሏቸው። የአላህ መልዕክተኛም «ዑመር ሆይ! አሁን አምነሃል» አሏቸው።

በሌላ ዘገባ ነብዩ (ﷺ):- «የኔና የኡመቶቼ ምሳሌ፤ ወደ ሚነድ እሳት እንዳይገቡ የእሳት እራቶችን እንደሚከላከል ነው። አንድ እሳት እንዳነደደና ሰውና በዚያ እሳት ላይ ቢራቢሮዎችና የእሳት እራቶች እንደሚወድቁበት አይነት ምሳሌ ነው። እኔ መታጠቂያችሁን ይዤ ለመከላከል ሞክሬ እናንተ ግን ለመግባት ትታገሉኛላችሁ» ብለዋል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ):- «ማንኛውንም ሙእምን በዱንያም ሆነ በአኺራ እኔ እቀርበዋለሁ፤ ከፈለጋችሁ ይህን (አንቀፅ) አንብቡ . ስለዚህ የትኛውም አማኝ ገንዘብ ካለው ዘመዶቹ ይውረሱት። ዕዳ ወይም ቤተሰብ ከተወ ግን አምጡልኝ እኔ ነኝ ኃላፊነቱን የምወስደው» ብለዋል።

وَإِذۡ أَخَذۡنَا مِنَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ مِيثَٰقَهُمۡ وَمِنكَ وَمِن نُّوحٖ وَإِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ
وَعِيسَى ٱبۡنِ مَرۡيَمَۖ وَأَخَذۡنَا مِنۡهُم مِّيثَٰقًا غَلِيظٗا ﴿٧﴾ لِّيَسۡـَٔلَ ٱلصَّٰدِقِينَ عَن صِدۡقِهِمۡۚ
وَأَعَدَّ لِلۡكَٰفِرِينَ عَذَابًا أَلِيمٗا ﴿٨﴾

**7-8.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከነብዮች የጠበቀ ኪዳናቸውን ከአንተም ከኑህም ከኢብራሂምም ከሙሳም ከመርየም ልጅ ዒሳም፣ በያዝን ጊዜ የሆነውን አስታውስ። ከእነርሱም የከበደን ቃል ኪዳን ያዝን። አላህ እውነተኞችን ከእውነታቸው ሊጠይቃቸው (ይህንን ሰራ)። ለከሓዲያንም አሳማሚን ቅጣት አዘጋጀ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَةَ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡ إِذۡ جَآءَتۡكُمۡ جُنُودٞ فَأَرۡسَلۡنَا عَلَيۡهِمۡ
رِيحٗا وَجُنُودٗا لَّمۡ تَرَوۡهَاۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرًا ﴿٩﴾ إِذۡ جَآءُوكُم مِّن فَوۡقِكُمۡ وَمِنۡ
أَسۡفَلَ مِنكُمۡ وَإِذۡ زَاغَتِ ٱلۡأَبۡصَٰرُ وَبَلَغَتِ ٱلۡقُلُوبُ ٱلۡحَنَاجِرَ وَتَظُنُّونَ بِٱللَّهِ ٱلظُّنُونَا۠ ﴿١٠﴾
هُنَالِكَ ٱبۡتُلِيَ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ وَزُلۡزِلُواْ زِلۡزَالٗا شَدِيدٗا ﴿١١﴾ وَإِذۡ يَقُولُ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ وَٱلَّذِينَ فِي
قُلُوبِهِم مَّرَضٞ مَّا وَعَدَنَا ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥٓ إِلَّا غُرُورٗا ﴿١٢﴾ وَإِذۡ قَالَت طَّآئِفَةٞ مِّنۡهُمۡ يَٰٓأَهۡلَ
يَثۡرِبَ لَا مُقَامَ لَكُمۡ فَٱرۡجِعُواْۚ وَيَسۡتَـٔۡذِنُ فَرِيقٞ مِّنۡهُمُ ٱلنَّبِيَّ يَقُولُونَ إِنَّ بُيُوتَنَا عَوۡرَةٞ وَمَا
هِيَ بِعَوۡرَةٍۖ إِن يُرِيدُونَ إِلَّا فِرَارٗا ﴿١٣﴾ وَلَوۡ دُخِلَتۡ عَلَيۡهِم مِّنۡ أَقۡطَارِهَا ثُمَّ سُئِلُواْ ٱلۡفِتۡنَةَ
لَأٓتَوۡهَا وَمَا تَلَبَّثُواْ بِهَآ إِلَّا يَسِيرٗا ﴿١٤﴾

**9-14.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ብዙ ሰራዊት በመጣባችሁና በእነርሱ ላይ ንፋስንና በአይናችሁ ያላያችሁትን ሰራዊት በላክን ጊዜ በናንተ ላይ ያደረገላችሁን ፀጋ (አስታውሱ)። ከበላያችሁም ከናንተ በታችም በመጡባችሁ፤ ጊዜ ዓይኖችም በቃበዙ፤ ልቦችም ወደ ላንቃዎች በደረሱና በአላህ መጥፎ ጥርጣሬዎችን በጠረጠራችሁ ጊዜ ያደረገላችሁን ፀጋ (አስታውሱ)። እዚያ ዘንድ አማኞች ተሞከሩ። ብርቱን መንቀጥቀጥም ተንቀጠቀጡ። መናፍቆችና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ሰዎች ሁሉ አላህና መልዕክተኛው ማታለልን እንጂ ሌላን አልቀጠሩንም በሚሉ ጊዜ (ያደረገላችሁን ውለታ አስታውሱ)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱም የሆነ ቡድን ጭፍሮች የየስሪብ ሰዎች ሆይ! ለእናንተ ስፍራ የላችሁምና ተመለሱ ባሉ ጊዜ (የሆነውን አስታውሱ)። ከእነርሱም መካከል ከፊሎቹ እርሷ ነውረኛ

ሳትሆኑ ቤቶቻችን ነውረኛ ናቸው በማለት ነብዩን ከጦሩ ለመመለስ ፈቃድን ይጠይቃሉ። መሸሸን እንጂ ሌላን አይፈልጉም። በእርሱም ላይ (በቤቶቻቸው) ከየቀበሌዋ ከጠላት በተገባባትና ከዚያ ከኢስላም መመለስን በተጠየቁ ኖሮ በፍጥነት በሰሯት ነበር። በእሷ ጥቂትን ጊዜ እንጂ አይቆዩም ነበር።

ከአህዛብ ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) የተቡክን ዘመቻ ሲያስቡና ውጡ ብለው ትዕዛዝ ሲሰጡ አንዳንድ ሰዎች «ወላጆቻችንን እናስፈቅድ» ማለት ሲጀምሩ ከአባትና ከእናት ትዕዛዝ የሚበልጠው ነብዩን (ﷺ) መታዘዝ መሆኑን ለመግለፅ ይህ አንቀፅ ወረደ።

ከአህዛብ ከ (10-11) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- በ 5 ኛው አመት ሂጅሪያ በሸዋል ወር ላይ ከመዲና ከሚኖሩ አይሁዶች የተወሰኑት ወደ ቁረይሾች በመጓዝ «ሙስሊሞችን እንዲዋጉና አነሳሱ አብረዋቸው እንደሚቆሙም ነገሯቸው። ከዚያም ወደ ገጠፋኖች ወደ ቀይስ ዐይኖች ወደ አሰዶች በመሄድ ሁላቸውም በአንድ ሆነው ነብዩን (ﷺ) ለመውጋት ተማማሉ ወደ መዲና መጡ። ነብዩ (ﷺ) ይህን ሲያውቁ ሙስሊሞችን አማከሩ። አል ፋሪስም በመዲና ከተማ ዙሪያ ምሽግ እንዲቆፍሮ ሀሳብ አቀረቡ ቁፈራው ተፈፀመ። ከዚያም የኸንደቅ (የአህዛብ) ዘመቻ ተካሄደ።
ይህ ዘመቻ የኸንደቅ ዘመቻ ተብሎ የተሰየመው ሰልማን አል. ፋሪሲይ የተባለው እውቅ ሰህባ በዚህ ጦርነት ላይ ጠላት ወደ መዲና ገብቶ እንዳያጠቃ ለማስቻል የመዲና ዙሪያ ጉድጓድ ቢቆፈር የተሻለ ነው ብሎ ባቀረበው ሀሳብ መሠረት ለጦርነቱ ስትራቴጂ ሲባል ጉድጓድ በመቆፈሩ ነው።

ከአህዛብ ምዕራፍ (12) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በአህዛብ ዘመቻ ዕለት ጠላት መዲናን የከበባት መሆኑ ሲነገራቸው መዲና በምስራቅ፣ በምዕራብና በደቡብ በጋራ የተከበበች ስለሆነች ጠላት ሊገባ የሚችለው በሰሜን በኩል ነው። ስለሆነም ይህን አቅጣጫ በምሽግ በመዝጋት መዲናን ለመጠበቅ ወስነው አርባ ክንድ ለአሥር ሰው በማከፋፈል እየተቆፈረ ሳለ የእነ ሰልማን ድርሻ በነበረው ክፍል አንዲት ነጭ ቋጥኝ አልሰበርም በማለቷ ለነብዩ (ﷺ) ተነገራቸው ነብዩም (ﷺ) መዶሻ አምጡልኝ በማለት ተቀብለው አንድ ጊዜ ሲመቱት በሁለቱ ጋራዎች መካከል ያለውን ቦታ ያሳየ ብርሃን ፈነጠቀ በዚህ ጊዜ እንዲሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ተከስቶ ቆጥኙም ተሰብሮ ወጣ በ (3) ኛው ጊዜ እንዲሁ ተመሳሳይ ሁኔታ ተከሰተ ከዚያ በኋላ ስለሁኔታው ሲጠየቁ «በ (1) ኛው ጊዜ የኪስራ ከተሞች፣ በ (2) ኛው የሮም ከተሞች፣ በ (3) ኛው የየመን ሕንጻዎች ታዩኝ፣ እናም መላኩ ጅብሪል ተከታዮቼ በነዚህ ሁሉ ላይ ድል እንደሚቀዳጁ ነገረኝ» ብለው ተናገሩ። አስመሳዮችም የሙሐመድ ነገር አይገርማችሁም ከመዲና እስከ ኪስራ ይታየኛል። ይላል ከዚህም አልፎ እናንተም ትቆጣጠሯታላችሁ ይላል። እናንተ ግን በሰፈራችሁ መኖር አቅቷችሁ ምሽግ እየቆፈራችሁ ነው። በማለት የሙስሊሞችን ሞራል የሚነካ ቃላት በመናገራቸው ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَلَقَدْ كَانُوا۟ عَـٰهَدُوا۟ ٱللَّهَ مِن قَبْلُ لَا يُوَلُّونَ ٱلْأَدْبَـٰرَ ۚ وَكَانَ عَهْدُ ٱللَّهِ مَسْـُٔولًا ﴿١٥﴾
قُل لَّن يَنفَعَكُمُ ٱلْفِرَارُ إِن فَرَرْتُم مِّنَ ٱلْمَوْتِ أَوِ ٱلْقَتْلِ وَإِذًا لَّا تُمَتَّعُونَ إِلَّا قَلِيلًا ﴿١٦﴾
قُلْ مَن ذَا ٱلَّذِى يَعْصِمُكُم مِّنَ ٱللَّهِ إِنْ أَرَادَ بِكُمْ سُوٓءًا أَوْ أَرَادَ بِكُمْ رَحْمَةً ۚ
وَلَا يَجِدُونَ لَهُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ وَلِيًّا وَلَا نَصِيرًا ﴿١٧﴾

**15-17.** ጀርባዎችንም ላያዞሩ ከዚያ በፊት በእርግጥ አላህን ቃል ኪዳን የገቡ ነበሩ። የአላህ ቃል ኪዳን የሚጠየቁበት ትልቅ ሀላፊነት ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሞት ወይም ከመገደል ብትሸሹ መሸሻችሁ ፈጽሞ አይጠቅማችሁም። ያን ጌዜም ጥቂትን እንጂ የምትጣቀሙ አትደረጉም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በእናንተ ላይ ክፉን ነገር ቢሻ ያ! ከአላህ የሚጠብቃችሁ ማነው? በላቸው ወይም ለናንተ ችሮታን ቢሻ (በክፉ የሚነካችሁ ማነው?) በላቸው። ከአላህም ሌላ ለእነርሱ ወዳጅም ሆነ ረዳት አያገኙም።

۞ قَدْ يَعْلَمُ ٱللَّهُ ٱلْمُعَوِّقِينَ مِنكُمْ وَٱلْقَآئِلِينَ لِإِخْوَٰنِهِمْ هَلُمَّ إِلَيْنَا ۖ وَلَا يَأْتُونَ ٱلْبَأْسَ
إِلَّا قَلِيلًا ﴿١٨﴾ أَشِحَّةً عَلَيْكُمْ ۖ فَإِذَا جَآءَ ٱلْخَوْفُ رَأَيْتَهُمْ يَنظُرُونَ إِلَيْكَ تَدُورُ أَعْيُنُهُمْ
كَٱلَّذِى يُغْشَىٰ عَلَيْهِ مِنَ ٱلْمَوْتِ ۖ فَإِذَا ذَهَبَ ٱلْخَوْفُ سَلَقُوكُم بِأَلْسِنَةٍ حِدَادٍ أَشِحَّةً عَلَى
ٱلْخَيْرِ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ لَمْ يُؤْمِنُوا۟ فَأَحْبَطَ ٱللَّهُ أَعْمَـٰلَهُمْ ۚ وَكَانَ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرًا ﴿١٩﴾

**18-19.** ከናንተ ውስጥ የሚያሳንፉትን ለወንድሞቻቸውም ወደ እኛ ኑ የሚሉትን ውጊያንም ጥቂትን እንጂ የማይመጡትን በእርግጥ አላህ ያውቃቸዋል። (እማኞች ሆይ!) በእናንተ ላይ እርዳታን የነፈጉ ሆነው እንጂ የማይመጡትን ሽብሩም በመጣ ጊዜ እነዚያ ከሞት መከራ በእርሱ ላይ የሚሸፍን አደጋ እንደ ወደቀበት ዓይኖቻቸው ወዲያና ወዲህ የምትንከራተት ሆና ወደ አንተ ሲመለከቱ ታያቸዋለህ። ሽብሩም በሄደ ጊዜ በገንዘብ ላይ የሚሳሱ ሆነው በተቡ ምላሶች ይነድፏባችኋል። እነዚያ አላመኑም። ስለዚህ አላህ ስራዎቻቸውን አበላሸ። ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።

يَحْسَبُونَ ٱلْأَحْزَابَ لَمْ يَذْهَبُوا۟ ۖ وَإِن يَأْتِ ٱلْأَحْزَابُ يَوَدُّوا۟ لَوْ أَنَّهُم بَادُونَ فِى ٱلْأَعْرَابِ
يَسْـَٔلُونَ عَنْ أَنۢبَآئِكُمْ ۖ وَلَوْ كَانُوا۟ فِيكُم مَّا قَـٰتَلُوٓا۟ إِلَّا قَلِيلًا ﴿٢٠﴾

**20.** መናፍቆች አህዛብን አልሄዱም ብለው ያስባሉ አህዛቦችም ቢመጡ እነርሱ በዘላኖች ውስጥ በገጠር የራቁ ሊሆን ይመኛሉ። ከወሬዎቻችሁ ይጠይቃሉ። በእናንተ ውስጥ በነበሩም ኖሮ ጥቂትን እንጂ አይዋጉም ነበር።

لَّقَدْ كَانَ لَكُمْ فِى رَسُولِ ٱللَّهِ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ لِّمَن كَانَ يَرْجُوا۟ ٱللَّهَ وَٱلْيَوْمَ ٱلْـَٔاخِرَ
وَذَكَرَ ٱللَّهَ كَثِيرًا ﴿٢١﴾

**21.** (እማኞች ሆይ)፣ ከናንተ መካከል አላህንና የመጨረሻውን ቀን የሚከጅል ለሆነና አላህንም በብዙ ለሚያወሳ ሰው ሁሉ በአላህ መልዕክተኛ መልካም መከተል አላችሁ።

وَلَمَّا رَءَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلْأَحْزَابَ قَالُوا۟ هَٰذَا مَا وَعَدَنَا ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ وَصَدَقَ ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥ ۚ وَمَا
زَادَهُمْ إِلَّآ إِيمَٰنًا وَتَسْلِيمًا ﴿٢٢﴾ مِّنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ رِجَالٌ صَدَقُوا۟ مَا عَٰهَدُوا۟ ٱللَّهَ عَلَيْهِ ۖ فَمِنْهُم
مَّن قَضَىٰ نَحْبَهُۥ وَمِنْهُم مَّن يَنتَظِرُ ۖ وَمَا بَدَّلُوا۟ تَبْدِيلًا ﴿٢٣﴾ لِّيَجْزِىَ ٱللَّهُ ٱلصَّٰدِقِينَ بِصِدْقِهِمْ
وَيُعَذِّبَ ٱلْمُنَٰفِقِينَ إِن شَآءَ أَوْ يَتُوبَ عَلَيْهِمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿٢٤﴾

**22-24.** አማኞችም አህዛብን ባዩ ጊዜ ይህ አላህና መልዕክተኛው የቀጠሩን ነው። አላህና መልዕክተኛውም እውነትን ተናገሩ አሉ። ይህ እምነትንና መታዘዝንም እንጂ ሌላን አልጨመረላቸውም። ከአማኞች በእርሱ ላይ ለአላህ ቃል ኪዳን የገቡበትን በእውነት የፈፀሙ ወንዶች አሉ ከእነርሱም ስለቱን የፈፀመ ለሃይማኖቱ የተገደለ አለ። ከእነርሱም ገና የሚጠባበቅ አለ የገቡትን ቃል መለወጥንም* አልለወጡም። አላህ እውነተኞችን በእውነተኛነታቸው ሊመነዳ መናፍቃንንም ቢፈልግ ሊቀጣ ወይም ቢመለሱ በእነርሱ ላይ ፀፀታቸቸውን ሊቀበል ይህን አደረገ። አላህ መሃሪና አዛኝ ነውና።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት አነስ ኢብኑ አን. ነድር ከበድር ጦርነት ቀርተው ነበር። ከዚያም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አጋሪያንን ለመጀመሪያ ጊዜ በተጋደሉበት ጦርነት ቀርቻለሁ። አላህ አጋሪያን ጋር የመዋጋትን እድል ቢሰጠኝ ኖሮ ምን አይነት ገድል እንደምሰራ በተመለከተከኝ ነበር» አላቸው። በኡሑድ ጦርነት ላይ ሙስሊሞች . (አልአሕዛብ፡ 23)
አሩበይዕ የምትባል የአነስ ኢብኑ ነድር እህት የአንዲት ሴትን የፊት ጥርሶች ሰበረችና የአላህ መልዕክተኛ ካሳ እንድትከፍል አዘዟት። አነስም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በእውነት በላከህ ጌታ ይሁንብህ የእህቴን የፊት ጥርሶች ለካሳ ሲባል አይሰበሩም። ምክንያቱም የተበዳይ ቤተሰቦቸች የደም ካሳ ለመቀበል ተስማምተዋልና» አላቸው። እሳቸውም«ከአላህ ባሪያዎች መካከል በአላህ ስም የፈፀሙት መሃላ ተቀባይትን የሚያገኙላቸው ሰዎች አሉ» አሉ።

وَرَدَّ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِغَيْظِهِمْ لَمْ يَنَالُوا۟ خَيْرًا ۚ
وَكَفَى ٱللَّهُ ٱلْمُؤْمِنِينَ ٱلْقِتَالَ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ قَوِيًّا عَزِيزًا ﴿٢٥﴾

**25.** እነዚያንም በአላህ የካዱትን በቁጭታቸው የተሞሉ መልካምን ነገር ያላገኙ ሆነው አላህ መለሳቸው። አማኞቹንም አላህ መጋደልን በቃቸው አላህ ብርቱና አሸናፊ ነውና።

**ከአህዛብ ምዕራፍ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-25) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህን መፍራት ተገቢ ስለመሆኑ፤
2. ለከሓዲያንና ለአስመሳዮች መታዘዝ ክልክል ስለመሆኑ፤
3. ቁርኣንና ሀዲስን መከተልና በአላህ ላይ መመካት ግዴታ ስለመሆኑ፤
4. በጃሂሊያ ዘመን የነበረውን ዚሃር መነሻ የሚወስድ ህግን ማውገዝ፤
5. ማንም ሰው በአባቱ ስም መጠራት እንዳለበት። በጉዲፈቻ የያዝነው ልጅም ቢሆን በአባቱ ስም እንጂ በሌላ መጠራት ክልክል መሆኑን፤
6. የጉዲፈቻን ልጅ በወላጅ አባቱ እንደሚጠራ፤
7. የጉዲፈቻ ልጅ አባቱ ካልታወቀ በኢስላም እንደሚጠራ፤
8. በስህተት ለተሰሩ ነገሮች አላህ እንደማይጠይቅ፤
9. ማንኛውም አማኝ የነብዩን ፍላጎት ከግል ፍላጎቱ ማስቀደም እንዳለበት፤
10. የነብዩ (ﷺ) ባለቤቶች ለማንም ወንድ መገባት እንደማይፈቀዱና ለሙዕሚኖች ሁሉ እንደ እናት እንደሆኑ፤
11. በኢስላም ምክንያት በሚገኝ ዝምድና መውረስ ስለመቅረቱ፤
12. ለማይወርሱ ሰዎች አንድ ሶስተኛም ሆነ ከዚያ በታች በሆነ ንብረት መናዘዝ እንደሚቻል፤
13. አላህን አንድ ማድረግና ሰዎችን ወደዚሁ ጥሪ መጥራት ግዴታ ስለመሆኑ፤
14. ነብያት ሁሉ ተውሒድን እንዲያስተምሩ ቃል ማስገባቱን፤
15. አፈግፋጊ አስመሳዮችን ማጋለጥና ማጥላላት፤
16. የአህዛብ ዘመቻ ዝርዝር በግልፅ ማስረዳትና በልዩ ሁኔታና መልክ ማቅረብ፤
17. የአህዛብ ዘመቻ ለሙስሊሞች በጣም ፈታኝ እንደነበር በግልፅ ማሳየት፤
18. አላህ ላይ ጥሩን ማሳብና መጠርጠር የተወደደ ስለመሆኑና አላህን በግፍ መጠርጠር ደግሞ ክህደትና ንፍቅና መሆኑን፤
19. ለማሸነፍ ይጥሩ የነበሩትን አስመሳዮች አቋም ለሙዕሚኖች መግለፅ፤
20. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
21. ቃልን ማክበር ግዴታ ስለመሆኑ፤
22. ጂሃድን መተው አላህ ከወሰነው ሞት እንደማያድን፤
23. ንፉግነትና ፈሪነት ከመናፍቃን ባህሪያት ስለመሆኑ፤
24. ወሬ ማብዛት የተጠላ ስለመሆኑ፤
25. ክህደት መልካም ተግባርን በሙሉ እንደሚያጠፋ፤
26. ክህደትና ንፍቅና ፍርሃትና ንፉግነት እንደማያዋጣ፤
27. ሙስሊሞች የአቅማቸውን ያህል ነብዩን ሊከተሉ እንደሚገደዱ፤
28. አላህ ሙስሊሞችን በአህዛብ ቀን የነበራቸውን አኩሪ አቋም ማስታወስ ማወደስ፤
29. የአህዛብ ጦርነት ምክንያቱን በግልፅ ማስተማሩን እንማራለን።

وَأَنزَلَ ٱلَّذِينَ ظَٰهَرُوهُم مِّنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ مِن صَيَاصِيهِمْ وَقَذَفَ فِى قُلُوبِهِمُ ٱلرُّعْبَ فَرِيقًا
تَقْتُلُونَ وَتَأْسِرُونَ فَرِيقًا ﴿٢٦﴾ وَأَوْرَثَكُمْ أَرْضَهُمْ وَدِيَٰرَهُمْ وَأَمْوَٰلَهُمْ وَأَرْضًا لَّمْ تَطَـُٔوهَا
وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرًا ﴿٢٧﴾

**26-27.** እነዚያንም ከመጽሐፉ ባለቤቶች አህዛቦችን የረዱቻቸውን (ቁረይዟን) ከምሽጎቻቸው አወረዳቸው በልቦቻቸውም ውስጥ መባባትን ጣለባቸው ከፊሉን ትገድላላችሁ፤ ከፊሉንም ትማርካላችሁ። ምድራቸውንም ቤቶቻቸውንም ገንዘቦቻቸውንም ገና ያልረገጣችኋትንም ምድር አወረሳችሁ። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ قُل لِّأَزۡوَٰجِكَ إِن كُنتُنَّ تُرِدۡنَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا وَزِينَتَهَا فَتَعَالَيۡنَ أُمَتِّعۡكُنَّ
وَأُسَرِّحۡكُنَّ سَرَاحٗا جَمِيلٗا ٢٨ وَإِن كُنتُنَّ تُرِدۡنَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَٱلدَّارَ ٱلۡأٓخِرَةَ فَإِنَّ ٱللَّهَ
أَعَدَّ لِلۡمُحۡسِنَٰتِ مِنكُنَّ أَجۡرًا عَظِيمٗا ٢٩ يَٰنِسَآءَ ٱلنَّبِيِّ مَن يَأۡتِ مِنكُنَّ بِفَٰحِشَةٖ
مُّبَيِّنَةٖ يُضَٰعَفۡ لَهَا ٱلۡعَذَابُ ضِعۡفَيۡنِۚ وَكَانَ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٗا ٣٠

**28-30.** አንተ ነብይ ሆይ፤ ለሚስቶችህ (እንዲህ) በላቸው ቅርቢቱን ህይወትና ጌጧን የምትፈልጉ እንደ ሆናችሁ ኑ። አጣቅማችኋለሁና መልካምንም ማሰማራት (በመፍታት)* አሰማራችኋለሁና። አላህንና መልዕክተኛውን የመጨረሻይቱን አገርም የምትፈልጉ ከሆናችሁ እነሆ አላህ ከናንተ ለመልካም ሰሪዎች ሁሉ ትልቅን ምንዳ አዘጋጅቷል። እናንተ የነብዩ ሚስቶች ሆይ፤ ከናንተ ውስጥ ግልፅ የሆነን መጥፎ ስራ የምትሰራ ሴት ቅጣቷ ሁለት እጥፍ ሆኖ ይነባበርባታል። ይህም በአላህ ዘንድ ገር ነው።

* (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ለሚስቶቻቸው ምርጫዎችን እንዲሰጡ በታዘዙበት ወቅት ከእኔ ጀመሩና እንዲህ አሉኝ «አንዳች ነገር እነግርሻለሁ። ወላጆችሽን ሳታማክሪ በፊት ውሳኔ ለመስጠት አትቸኩይ» አሉኝ። እሳቸው የእኔ ቤተሰቦች እሳቸውን ተይ ብለው እንደማያዙኝ በሚገባ ያውቃሉ። አክለውም «አላህ እንዲህ ብሏል፤ «አንተ ነብይ ሆይ! ለሚስቶችህ እንዲህ በላቸው፡- ቅርቢቱን ሕይወትን ጌጧን የምትፈልጉ እንደሆናችሁ ኑ አጣቅማችኋለሁና፤ መልካምን ማሰማራት (በመፍታት) አሰማራችኋለሁና፤ አላህንና መልዕክተኛውን የመጨረሻውን አገርም የምትፈልጉ ብትሆኑም እነሆ አላህ ከናንተ ለመልካም ስራዎቹ ትልቅን ምንዳ አዘጋጅቷል» (አል. -አሕዛብ 28-29) እኔም ስለዚህ ምንድ ነው ቤተሰቦቼን የማማክራቸው?እኔ እኮ አላህን፤ መልዕክተኛውንና ዘልዓለማዊ ሕይወት እፈልጋለሁ»፤ አልኳቸው። እኔ እንደፈፀምኩት ሌሎቹም የነብዩ ሚስቶች ፈፀሙ»

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻህ እንዳስተላለፉት «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ለሚስቶቻቸው ከእርሳቸው ጋር መቆየትን ወይም ከርሳቸው መፈታትን አስመልክቶ ምርጫዎችን አቀረቡልን ሁላችንም አላህንና መልዕክተኛውን መረጥን። ያን ምርጫ ማቅረባቸው ግን ልክ እንደ ፍቺ አያስቆጥረውም።»

ከአህዛብ ምዕራፍ (23) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አነስ ኢብኑ ማሊክ «አነስ ኢብኑ ነድር የሚባል አጎት ነበረኝ። ይህንንም ስም የገኘሁት በሱ ስም ለመጠራት ተብሎ ነው» ብለዋል። «ይኸው አጎቴ በበድር ዘመቻ ሳይገኝ በመቅረቱ በጣም ተሰምቶት ለአላህ እንዲህ ሲል ቃል ገባ። አላህ ጦርነት

ካጋጠመኝ ማንነቴን አሳየዋለሁ» በማለት ከዚያ በአመቱ የኡሁድ ዘመቻ ደረሰና ሙስሊሞች ገሸሽ ሲሉ አነስ እንዲህ አለ «ጌታዬ ሆይ! ከሓዲያን ከፈፀሙት ደባ እራሴን ነፃ አወጣለሁ ሙስሊሞች ካደረጉት ይቅርታ እጠይቃለሁ» በማለት ሰይፉን መዞ ወደ ጦር ግንባር ሲገሰግስ ሰዕድ ኢኢብኑ ሙዓዘን አገኘውና «ስዕድ ሆይ! እሁድ አጠገብ ጀነት ይሸተኛል ካለው በኋላ እስከ መጨረሻ ትንፋሹ ድረስ ተዋጋቸውና ሞት ከሰማንያ ሶስት እስከ ሰማንያ ዘጠኝ የሚሆን ቁስል በአካሉ ላይ ተገኘ። በጦር አካሉን እንኳን ቆራርጠውት ስለነበር ማንነቱን ለመለየት አቅቶን እህቱ ነበረች በጣቶቹ የለየችው። እሱንና መሰሎቹን በተመለከተ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

۞وَمَن يَقْنُتْ مِنكُنَّ لِلَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَتَعْمَلْ صَٰلِحًا نُّؤْتِهَآ أَجْرَهَا مَرَّتَيْنِ وَأَعْتَدْنَا لَهَا رِزْقًا كَرِيمًا ﴿٣١﴾ يَٰنِسَآءَ ٱلنَّبِيِّ لَسْتُنَّ كَأَحَدٍ مِّنَ ٱلنِّسَآءِ إِنِ ٱتَّقَيْتُنَّ فَلَا تَخْضَعْنَ بِٱلْقَوْلِ فَيَطْمَعَ ٱلَّذِى فِى قَلْبِهِۦ مَرَضٌ وَقُلْنَ قَوْلًا مَّعْرُوفًا ﴿٣٢﴾ وَقَرْنَ فِى بُيُوتِكُنَّ وَلَا تَبَرَّجْنَ تَبَرُّجَ ٱلْجَٰهِلِيَّةِ ٱلْأُولَىٰ وَأَقِمْنَ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتِينَ ٱلزَّكَوٰةَ وَأَطِعْنَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓ إِنَّمَا يُرِيدُ ٱللَّهُ لِيُذْهِبَ عَنكُمُ ٱلرِّجْسَ أَهْلَ ٱلْبَيْتِ وَيُطَهِّرَكُمْ تَطْهِيرًا ﴿٣٣﴾ وَٱذْكُرْنَ مَا يُتْلَىٰ فِى بُيُوتِكُنَّ مِنْ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ وَٱلْحِكْمَةِ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ لَطِيفًا خَبِيرًا ﴿٣٤﴾

**31-34.** ከናንተም መካከል ለአላህና ለመልዕክተኛው የምትታዘዝ መልካም ስራንም የምትሰራ ምንዳዋን ሁለት ጊዜ እንሰጣታለን። ለእርሷም የከበረን ሲሳይ አዘጋጅተንላታል። የነብዩ መሐመድ ሴቶች ሆይ! እንደ ማናቸውም ሴቶች አይደላችሁም። አላህን ብትፈሩ ትበልጣላችሁ ያ! በልቡ ውስጥ በሽታ ያለበት እንዳይከጅል በንግግር አትለስልሱም መልካምንም ንግግር ተናገሩ። በቤቶቻችሁም ውስጥ እርጉ እንደ ፊተኛይቱ መሃይምነት ጊዜ መገለጥም (በማጌጥ) አትገለጡ ሶላትንም በደንቡ ስገዱ ዘካንም ስጡ አላህንና መልክተኛውንም ታዘዙ የነብዩ ቤተሰቦች ሆይ፣ አላህ የሚሻው ከናንተ ላይ ርክሰትን ሊያስወግድና ማጥራትንም ሊያጠራችሁ ብቻ ነው። ከአላህ አንቀፆችና ከጥበቡም በቤቶቻችሁ የሚነበበውን አስታውሱ። አላህ እዝነቱ ረቂቅ፤ ውስጠ አዋቂ ነውና።

ከአህዛብ ምዕራፍ (28-32) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አንድ ቀን አቡበከር ሲዲቅ ወደ ነብዩ መሐመድ (ﷺ) ቤት በመምጣት ለመግባት ፍቃድ ጠይቀው ሳይፈቀድላቸው በር ላይ እንደቆሙ ዑመር ኢብኑልኸጧብ መጡ። ሁለቱም በአንድ ጊዜ ተፈቅዶላቸው ሲገቡ የነብዩ ባለቤቶች ዱንያ ለመጠየቅ በአንድ ላይ ተሰባስበው ነብዩን በመጠየቅ ላይ ደረሱ። ዑመር የነብዩን ቁጣ ሲያዩ አንድ ነገር ተናግሬ እሳቸውን ማሳቅ አለብኝ ብዬ ወሰንኩና «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! የዘይድ ልጅ ዛሬ ቢያይዋት ወጪ ስትጠይቀኝ ተነስቼ አንገቷን በቦክስ አልኳት አሉ። ነብዩ ፈገግ አሉና «ይኸው እነሱንስ አታያቸውም ወጪ እየጠየቁኝ» አሉ። በዚህ ጊዜ አቡበከር ወደ ልጃቸው ዓኢሻ ሲሄዱ ዑመርም ወደ ልጃቸው ሐፍሷ ሄዱና ነብዩ የማይችሉትን

ትጠይቃላችሁን በማለት ዱላ ቀረሽ ወቀሳ ወቀሷቸው። ከዚህ በኋላ ወላሂ የሌላቸውን ነገር አንጠይቅም በማለት ማሉ። በዚህ ጊዜ እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። በዚህ ጊዜም ነብዩ በዓኢሻ በመጀመር ምርጫውን ማቅረብ ጀመሩ። ዓኢሻን ጠርተው «አንድ ነገር ልነግርሽ ነውና ሳትቸኩይ ወላጆችሽን አማክረሽ እንድትወስኝ አደራ እልሻለሁ» በማለት ጀመሩላቸው። ዓኢሻም ምንድ ነው ያ ረሱላህ ስላቸው ነብዩም እንዚህን አናቅፅ አነበቡ። በዚህ ጊዜ ዓኢሻ በርስዎ ጉዳይ ነው አባትና እናቴን የማማክረው እኔ አላህን፤ መልዕክተኛውንና አኼራዬን መርጫለሁ በማለት መለሱላቸው። በጊዜው የነበሩ ዘጠኙ ሚስቶቻቸው ዓኢሻ የመረጡትን መረጡ።

إِنَّ ٱلْمُسْلِمِينَ وَٱلْمُسْلِمَٰتِ وَٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتِ وَٱلْقَٰنِتِينَ وَٱلْقَٰنِتَٰتِ وَٱلصَّٰدِقِينَ
وَٱلصَّٰدِقَٰتِ وَٱلصَّٰبِرِينَ وَٱلصَّٰبِرَٰتِ وَٱلْخَٰشِعِينَ وَٱلْخَٰشِعَٰتِ وَٱلْمُتَصَدِّقِينَ وَٱلْمُتَصَدِّقَٰتِ
وَٱلصَّٰٓئِمِينَ وَٱلصَّٰٓئِمَٰتِ وَٱلْحَٰفِظِينَ فُرُوجَهُمْ وَٱلْحَٰفِظَٰتِ وَٱلذَّٰكِرِينَ ٱللَّهَ كَثِيرًا
وَٱلذَّٰكِرَٰتِ أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُم مَّغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًا ﴿٣٥﴾

**35.** ሙስሊም ወንዶችና ሙስሊም ሴቶች ምዕመናንና ምዕመናትም ታዛዦች ወንዶችና ታዛዦች ሴቶች እውነተኞች ወንዶችና እውነተኞች ሴቶች ታጋሽ ወንዶቸችና ታጋሽ ሴቶች አላህን ፈሪ ወንዶችና አላህን ፈሪ ሴቶች መጽዋቾች ወንዶችና መጽዋቾች ሴቶች ጿሚ ወንዶችና ጿሚ ሴቶች ካልተፈቀደ ስራ ብልቶቻቸውን ጠባቂ ወንዶችና ጠባቂ ሴቶች አላህን በብዙ አውሺ ወንዶችና አውሺ ሴቶች አላህ ለእነርሱ ምህረትንና ታላቅን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል።

**ከአህዛብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (26-35) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የክህደትን አስከፊነት መጨረሻ ማሳየት፤
2. የአላህን ቃል ተፈፃሚነት በግልፅ ማሳየት፤
3. የአላህ ኃይል በምንም ሊገታ እንደማይቻል ማሳወቅ፤
4. ሚስቶች ካስቸገሩ ማማረጥ ተገቢ ስለ መሆኑና ፍቺን ከመረጡ እንደሚፈቱ ካልመረጡት እንደማይፈቱ፤
5. አላህ ለነብዩ (ﷺ) የነበረውን ልዩ ክብርና እንክብካቤ፤
6. ነብዩ (ﷺ) በዚህ ነገር በሴቶች ሀቅ ከመጠየቅ ነፃ መውጣታቸው፤
7. አላህ ለነብዩ (ﷺ) ቀድሞውኑ ዱንያን ከሚመርጡ ሴት እንደጠበቃቸው፤
8. የነብዩ (ﷺ) ባለቤቶች ሁሉም አላህን ከሚያስቆጣ ነገር ሁሉ ይጠነቀቁ እንደነበር፤
9. የነብዩ (ﷺ) ባለቤቶች ሁሉም በነበራቸው ቆራጥነት እንዷ እንኳን መፋታትን እንዳልፈለገች፤
10. ከፍች በኋላ እንዳቅም የሞራል መጠበቂያ አንድ ነገር ማድረግ እንደሚገባ፤
11. (ሙትዐ) የሞራል ካሳ መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ፤
12. በትዳርም ሆነ በሌላ ነገር ማስመረጥ ተገቢ ስለመሆኑ፤
13. የአዋቂ ስህተት ከአላዋቂ ስህተት የከፋ ስለመሆኑ፤
14. ነብዩ (ﷺ) ለባለቤቶቻቸው ይህን ምርጫ በመስጠት ያሳዩት የሴትን ልጅ ነፃነት፤
15. ትልቅነት በአላህ ፍራቻ ብቻ ስለመሆኑ፤

16. ሴት አማኝንም ሆነ ወንዶችን በአላህ በኩል ምህረት ማብሰር፤
17. ሴት ልጅ ድምፅዋን በማቅጠን በመሰባበር (በመሽኮርመም) ከባእድ ወንድ ጋር መነጋገሯ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
18. በጣም አንገብጋቢ ካልሆነ በስተቀር ሴት ልጅ ከቤት መውጣት እንደማያስፈልጋት፤
19. ሴት ልጅ አጊጣና ተውባ ጌጧን እያሳየችና ለወንዶች በሚስብ መልኩ መጓዟ የተከለከለ ስለ መሆኑ፤
20. ማንም ሙስሊም አላህ የለገሰውን ክብርና የእምነት ልብስ በማስታወስ ራሱን ከመጥፎ ነገር መጠበቅ እንዳለበት፤
21. ጥበብ ማለት የታላቁ ነብዩ (ﷺ) ትክክለኛ ሀዲስ ስለመሆኑ፤
22. ዳግም የድንቁርና ዘመን እንደሚመጣ አሁን ወደ ተከሰተው የእርጅና ዘመን መጠቆም፤
23. በዚህ አንቀፅ የተወሳችው መልካም ባሪያ በአላህ ዘንድ ምን ያህል ክብር እንዳላት እንማራለን።

وَمَا كَانَ لِمُؤۡمِنٖ وَلَا مُؤۡمِنَةٍ إِذَا قَضَى ٱللَّهُ وَرَسُولُهُۥٓ أَمۡرًا أَن يَكُونَ لَهُمُ ٱلۡخِيَرَةُ مِنۡ أَمۡرِهِمۡۗ
وَمَن يَعۡصِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَقَدۡ ضَلَّ ضَلَٰلٗا مُّبِينٗا ٣٦

**36.** አላህና መልዕክተኛው በአንድ ነገር ላይ በወሰኑ ጊዜ ለምዕምናንና ለምዕመናት ከነገራቸው ለእነርሱ ከመቀበል ዉጭ ምንም ምርጫ ሊኖራቸው አይገባም። የአላህንና የመልክተኛውን ትእዛዝ የጣሰ ሰው ሁሉ ግልፅ የሆነን መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ።

وَإِذۡ تَقُولُ لِلَّذِيٓ أَنۡعَمَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ وَأَنۡعَمۡتَ عَلَيۡهِ أَمۡسِكۡ عَلَيۡكَ زَوۡجَكَ وَٱتَّقِ ٱللَّهَ وَتُخۡفِي
فِي نَفۡسِكَ مَا ٱللَّهُ مُبۡدِيهِ وَتَخۡشَى ٱلنَّاسَ وَٱللَّهُ أَحَقُّ أَن تَخۡشَىٰهُۖ فَلَمَّا قَضَىٰ زَيۡدٞ مِّنۡهَا
وَطَرٗا زَوَّجۡنَٰكَهَا لِكَيۡ لَا يَكُونَ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ حَرَجٞ فِيٓ أَزۡوَٰجِ أَدۡعِيَآئِهِمۡ إِذَا قَضَوۡاْ مِنۡهُنَّ
وَطَرٗاۚ وَكَانَ أَمۡرُ ٱللَّهِ مَفۡعُولٗا ٣٧

**37.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለዚያም አላህ በእርሱ ላይ ለለገሰለትና አንተም (ነጻ በማውጣት) በርሱ ላይ ለለገስክለት ሰው* አላህ ገላጩ የሆነን ነገር በነፍስህ ውስጥ የምትደብቅና አላህን ልትፈራው ይልቅ የተገባው ሲሆን ሰዎችን የምትፈራ ሆነህ ሚስትህን ባንተ ዘንድ ያዝ። (ከመፍታት) አላህንም ፍራ በምትል ጊዜ (አስታውስ)። ዘይድም ከእርሷ ጉዳዩን በፈፀመ ጊዜ በምዕመኖች ላይ ልጅ አድርገው ባስጠጓቸው ሰዎች ሚስቶች ከእነርሱ ጉዳይን በፈፀሙ ጊዜ በማግባት ችግር እንዳይደርስባቸው እርሷን አጋባንህ (ዳርንህ)። የአላህ ትእዛዝ ተፈጻሚ ነው።

* ይህ ሰው ዘይድ ኢብኑ አል ሃሪስ ይባላል። ሚስቱ ዘይነብ ቢንት ጀህሽ ትባላለች።

مَّا كَانَ عَلَى ٱلنَّبِيِّ مِنْ حَرَجٍ فِيمَا فَرَضَ ٱللَّهُ لَهُۥ ۖ سُنَّةَ ٱللَّهِ فِى ٱلَّذِينَ خَلَوْا۟ مِن قَبْلُ ۚ وَكَانَ أَمْرُ ٱللَّهِ قَدَرًا مَّقْدُورًا ﴿٣٨﴾ ٱلَّذِينَ يُبَلِّغُونَ رِسَـٰلَـٰتِ ٱللَّهِ وَيَخْشَوْنَهُۥ وَلَا يَخْشَوْنَ أَحَدًا إِلَّا ٱللَّهَ ۗ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ حَسِيبًا ﴿٣٩﴾ مَّا كَانَ مُحَمَّدٌ أَبَآ أَحَدٍ مِّن رِّجَالِكُمْ وَلَـٰكِن رَّسُولَ ٱللَّهِ وَخَاتَمَ ٱلنَّبِيِّـۧنَ ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمًا ﴿٤٠﴾

**38-40.** በነብዩ ላይ አላህ ለእርሱ በፈረደው ነገር ምንም ችግር ሊኖርበት አይገባም። በእነዚያ ከዚያ በፊት ባለፉት ነብያት አላህ ደነገገው የአላህም ትእዛዝ የተፈረደ ፍርድ ነው። ለእነዚያ የአላህን መልዕክቶች ለሚያደርሱና ለሚፈሩት ከአላህ በስተቀርም አንድንም ለማይፈሩት ተደነገገ ተቆጣጣሪነትም በአላህ በቃ። (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ)፣ ሙሐመድ ከወንዶቻችሁ የአንድም ሰው አባት አይደለም። ግን የአላህ መልዕክተኛና የነብያት መደምደሚያ ነው። አላህ በነገሩ ሁሉ አዋቂ ነው።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱذْكُرُوا۟ ٱللَّهَ ذِكْرًا كَثِيرًا ﴿٤١﴾ وَسَبِّحُوهُ بُكْرَةً وَأَصِيلًا ﴿٤٢﴾ هُوَ ٱلَّذِى يُصَلِّى عَلَيْكُمْ وَمَلَـٰٓئِكَتُهُۥ لِيُخْرِجَكُم مِّنَ ٱلظُّلُمَـٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ ۚ وَكَانَ بِٱلْمُؤْمِنِينَ رَحِيمًا ﴿٤٣﴾

**41-43.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህን ብዙ ማውሳትን አውሱት።* በቀኑ መጀመሪያና መጨረሻ አጥሩት። እርሱ ያ፣ በእናንተ ላይ እዝነትን የሚያወርድ ነው። መላእክቶችም እንደዚሁ ምህረትን የሚለምኑላችሁ ናቸው። ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣችሁ ዘንድ (ያዝንላችኋል)። ለምእመናንም በጣም አዛኝ ነው።

✴ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ላኢላሀ ኢለ ሏህ ወሕደሁ ላ ሸሪይከ ለሁ፤ ለሁል ሙልክ ወለሁል ሐምዱ ወሁወ ዐላ ኩልሊ ሸኢን ቀዲይር አስር ጊዜ ያለ ከኢስማኢል ልጆች ውስጥ አራት ነፍሶችን ከባርነት ነፃ እንደለቀቀ ይቆጠርለታል»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የኢስራእ ጉዞ ባደረግኩበት ሌሊት ኢብራሂምን አገኘሁት «ሙሐመድ ሆይ! በተከታዮችህ ሰላምታ አድርስልኝ። ጀነት አፈሯ ጥሩ፤ ውሀዋ ጣፋጭ፤ መስኳ ሰፊ፤ አትክልቷ ሱብሐነላህ ወልሐምዱሉላህ ወላ ኢላሀ ኢልለላህ፤ ወልላሁ አክበር፤ መሆኑንም ንገራቸው» አለኝ።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻ እንዳስተላለፉት«የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ሆነው አላህን ያወሱና ያወድሱ ነበር።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሲነጋና ሲመሽ መቶ ጊዜ፡- ሰብሐነልላህ ወቢሐምዲሂ ያለ እንደርሱ ወይም ከርሱ በላይ ይህን ቃል ያለ ሲቀር ሌላው ሰው ከርሱ የላቀ ደረጃ ይዞ በዕለተ ቂያማ አይመጣም።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት አንድ ሰው ከነብዩ ዘንድ መጣና፡- «የአላህ

መልዕክተኛ ሆይ! ባለፈው ሌሊት ከባድ ነገር አጋጠመኝ። አንዲትን ጊንጥ ነከሰችኝ»አላቸው። እርሳቸውም፦ ምሽት ላይ «አዑዙ ቢከሊማቲልላሂ አት. ታምማቲ ሚን ሸርሪ ማ ኸለቅ»፤ ብለህ ቢሆን ኖሮ አትጎዳህም ነበር አሉት።

አቡ ዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት ነብዩ ንጋት ላይ እንዲህ ይሉ ነበር፦ «አልላሁምመ ቢከ አስበሕና ወቢከ አምበይና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙውቱ ወኢለይከ አን. ነሹውር» ሲመሽ ደግሞ እንዲህ ይሉ ነበር፦ «አልላሁምመ ቢከ አምሰይና ወቢከ ነሕያ ወቢከ ነሙውቱ ወኢለይከ መሲይር»

አቡ ዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አቡበክር ሲድቅ እንዳስተላለፉት«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በንጋትና በምሽት የምላቸውን ቃላት ይንገሩኝ» አላቸው። መልዕክተኛውም እንዲህ አዘዙት፦ «አልላሁምመ ፋጢረ ስ. ሰማዊቲ ወል. አርዲ ዓመል. ገይቢ ወሽ. ሸሃደቱ ረብበ ኩልሊ ሸይኢን ወመሊይከሁ አሽሀዱ አን ላ ኢላህ ኢልላ አንተ አዑዙ ቢከ ሚን ሸርሪ ነፍሲይ ወሸርሪ አሽ. ሸይጣኒ ወሺርኪሂ።» «ስትነጋ፤ ስታመሽና ወደ መኝታህ ስትሄድ እነዚህን ቃላት በል» አሉትም።

አቡ ዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ዑስማን ብኑ ዐፋን እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «አንድ የአላህ ባሪያ በየቀኑ ጠዋትና ማታ ሶስት ሶስት ጊዜ፦ ቢስሚልላሂ አልለዚይ ላ የዱርሩ መዐ ኢስሚሂ ሸይኡን ፊይል ወላ ፊይል ሰሚኢ ወሁስ ሰሚይዑል. ዐሊይም፤ ካለ ምንም ነገር አይጎዳውም»

አቡዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ በሺር እንዳስተላለፉት ነብዩ እንዲህ ብለዋል፦ «ዱዓ አምልኮት ነው»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት ነብዩ በብዛት የሚያደርጉት ዱዓ የሚከተለው ነበር፦ «አልላሁምመ አቲና ፊይድ. ዱንያ ሐሰነተን ወፊይል. አኺረቲ ሐሰነተን ወቂና ዐዛበን. ናር።»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) «ከዳውድ ዱዓዎች መካከል የሚከተለው ይገኝበታል» በማለት ተናግረዋል፦ «አልላሁምም ኢንኒይ አስአሉከ ሑብበከ ወሑብበ መን ዩሒብቡከ ወልዐመለ አልለዚይ ዩበልሊጉኒይ ሑብበከ አልላሁምመ ኢጅዐል ሑብበከ አሐብበ ኢለይየ ሚን ነፍሲይ ወአህሊ.ይ ወሚነል. ማኢል. ባሪድ።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ የሚከተለውን ሲናገሩ ሰምቻለሁ በማለት አቡ ደርዳእ አስተላልፈዋል፦ «አንድ ሙስሊም የአላህ አገልጋይ ከአጠገቡ ለሌላ ወንድሙ ዱዓ በሚያደርግ ጊዜ መልአከው፦ ለርሱ የጠየቅከለት ነገር ለአንተም ይሰጥህ ለዋ።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ. ደርዳእ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይሉ ነበር፦ «አንድ ሙስሊም ከአጠገቡ ለሌላ ወንድ የሚያደርገው ዱዓ ተቀባይነት አለው። ከራሱ ላይ ለዚሁ ተግባር የተሰየመ መልአክ አለ። ሰውየው ለወንድሙ በበጎ ነገር ዱዓ ባደረገለት ቁጥር መልአከው፦ አሚን፤ ለርሱ የጠየቅከለትን ነገር ላንተም ይሰጥህ ይላል።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ «ራሳችሁን፤ ልጆቻችሁን ወይም ንብረታችሁን አትርገሙ። ምናልባትም አላህ ዱዓን በሚቀበልበት ወቅት ይህን የፈፀማችሁትን አጋጣሚ ተፈጥሮ አላህ እርግማናችሁን ሊቀበል ይችላልና።»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕተኛ «ይበልጥ ተሰሚነት ያለው ዱዓ የትኛው ነው?» ተብለው ተጠይቀው፦ «ከሌሊቱ መሐልና ከግዴታ ሶላቶች በኋላ የሚደረግ ዱዓ» በማለት መለሱ።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ «ንፅህና የእምነት ግማሽ ነው። አልሐምዱ ሊልላህ ሚዛን ትሞላለች። አልሐምዱ ሊልላህ እና ሰብሓነልላህ በምድርና በሰማይ መካከል ያሉ ቦታዎችን ይሞላሉ፡»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ሰዕድ ኢብ አቢ ወቃስ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፡- አንድ በደዊን ወደ አላህ መልዕክተኛ መጣና «ደጋግሜ የምለውን ቃል ያስተምሩኝ» አላቸው። «ላ ኢላሀ ኢልለልላሁ ወሕደሁ ላ ሸሪይከ ለሁ አልላሁ አክበር ከቢራ ወልሐምዱ ሊልላ ከሰይራ ወሰብሐነልላሂ ረብል ዓለሚን ወላ ሐውለ ወላ ቁውወተ ኢላል ቢልላሂል ዐዚይዚል ሐኪይም፤ በል» አሉት። «እነዚህ ለአምላኬ ናቸው። ለኔስ?» አላቸው። «አልላሁምመ ኢግፊር ሊይ ወርሐምኒይ ወርዙቅኒይ በል» አሉት።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ንፅህና የእምነት ግማሽ ነው። አልሐምዱ ሊልላህ ሚዛን ትሞላለች። አልሐምዱ ሊልላህ እና ሰብሓነልላህ በምድርና በሰማይ መካከል ያሉ ቦታዎችን ይሞላል።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ከሙሀጂሮች መካከል ድሆች ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ቀረቡና እንዲህ በማለት ጠየቋቸው። «ባለሀብቶች የላቀ ደረጃና ዘልዓለማዊ ፀጋን አገኙ። ምክንያቱም ልክ እንደኛው ይሰግዳ። ልክ እንደኛው ይፆማሉ ግና አነርሱ የገንዘብ ብልጫ ስላላቸው ሐጅና ዑራን ይፈፅማሉ፤ ይታገላሉ። ይመፀውታሉ» መልዕክተኛውም «የቀደማችሁን ምትደርሱበት ከኋላችሁ ያሉትን የምትቀድሙበት፤ እንደ እናንተ የሰራ ካልሆነ በስተቀር ማንም ከናንተ እኩል የማይሆንበት ስራ ላስተምራችሁን?» አሏቸው። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ያስተምሩን» አሉ። መልዕክተኛውም «ከየሶላቱ በኋላ ሰላሳ ሶስት ጊዜ ተስቢህ ተሕድና ተከብር አድርጉ» አሉ። ሐዲሱን ከአቡ ሁረይራህ በማድመጥ ያስተላፉት አቡ ሳለሕ ስለነዚህ ዝክሮች አባባል ተጠይቀው ሲመልሱ፡- ሰብሐነልላህ፤ አልሐምዱሊላህ፤ አልላሁ አክበር፤ እያንዳንዳቸው ሰላሳ ሶስት ጊዜ ይበል፤ በማት መልሰዋል።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ሰዕድ ኢብኑ አቢ ወቃስ እንዲህ ሲሉ አስተላፈዋል፡- ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ነበርን ከእናንተ አንዳችሁ በየቀኑ አንድ ሺህ በጎ ስራን መሸመት ይሳነዋልን? በማለት ጠየቁን። ከታዳሚዎች አንዱ፡- «አንድ ሺህ በጎ ስራ መሸመት የሚችለው እንዴት ነው?» አላቸው። እርሳቸውም ሲመልሱ፡- «መቶ ተስቢሕ ሲያደርግ አንድ ሺህ የበጎ ስራ ምንዳ ይፃፍለታል። ወይም አንድ ሺህ ኃጢአቶች ይታበሱለታል።»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ዘር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «እያንዳንዳችሁ ሁሉም የአካል ክፍሎች ምፅዋት የፀናባቸው ሆኖ ያነጋሉ። እያንዳንዱ ተስቢህ ሶደቃ ነው። እያንዳንዱ ተሕሚይድ ሰዶቃ ነው። እያንዳንዱ ተህሊይል ሶደቃ ነው። እያንዳንዱ ተክቢይር ሶደቃ ነው። በመልካም ማዘዝ ሶደቃ ነው። ከክፉ መከልከል ሶደቃ ነው። በረፋዱ ወቅት የሚሰገዱ ሁለት ረከዓዎች ከዚህ ሁሉ ያብቃቃሉ።»

تَحِيَّتُهُمْ يَوْمَ يَلْقَوْنَهُۥ سَلَٰمٌۚ وَأَعَدَّ لَهُمْ أَجْرًا كَرِيمًا ﴿٤٤﴾

**44.** በሚገናኙበት ቀን መከባበሪያቸው ሰላም መባባል ነው። ለእነርሱም የከበረን ምንዳ አዘጋጅቶላቸዋል።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِنَّآ أَرْسَلْنَٰكَ شَٰهِدًا وَمُبَشِّرًا وَنَذِيرًا ﴿٤٥﴾ وَدَاعِيًا إِلَى ٱللَّهِ بِإِذْنِهِۦ وَسِرَاجًا
مُّنِيرًا ﴿٤٦﴾ وَبَشِّرِ ٱلْمُؤْمِنِينَ بِأَنَّ لَهُم مِّنَ ٱللَّهِ فَضْلًا كَبِيرًا ﴿٤٧﴾ وَلَا تُطِعِ ٱلْكَٰفِرِينَ
وَٱلْمُنَٰفِقِينَ وَدَعْ أَذَىٰهُمْ وَتَوَكَّلْ عَلَى ٱللَّهِۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ وَكِيلًا ﴿٤٨﴾

**45-48.** አንተ ነብይ ሆይ! እኛ መስካሪ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ላክንህ። ወደ አላህም በፈቃዱ ጠሪ አብሪና ብርሃን አድርገን ላክንህ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አማኞችንም ከአላህ ዘንድ ለእነርሱ ታላቅ ችሮታ ያላቸው መሆኑን አብስራቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲያንና መናፍቃንንም አትታዘዛቸው ማሰቃየታቸውንም (ለአላህ) ተው። በአላህ ላይ ተጠጋ መጠጊያነትም በአላህ በቃ።*

* እዚህ ላይ በዐረበኛው በአባትና በእናት በኩል የሚዛመዱትን አጎቶችና አክስቶች በመለየት የሚተረጎም አለው። በአማርኛችን ሁሉም አጎት፤ አክስት በመባል የሚታወቅ ስለሆነ በዚሁ አልፈዋለሁ።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا نَكَحۡتُمُ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتِ ثُمَّ طَلَّقۡتُمُوهُنَّ مِن قَبۡلِ أَن تَمَسُّوهُنَّ فَمَا لَكُمۡ عَلَيۡهِنَّ مِنۡ عِدَّةٖ تَعۡتَدُّونَهَاۖ فَمَتِّعُوهُنَّ وَسَرِّحُوهُنَّ سَرَاحٗا جَمِيلٗا ﴿٤٩﴾

**49.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ምዕመናትን ባገባችሁና ከዚያ ሳትነኳቸው በፊት በፈታችኋቸው ጊዜ ለናንተ በእነርሱ ላይ የምትቆጥሩዋት ዒዳ ምንም የላችሁም። ሆኖም (አጣቅሟቸው) ጉርሻ ስጧቸው። መልካም ማሰናበትንም አሰናብቷቸው።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِنَّآ أَحۡلَلۡنَا لَكَ أَزۡوَٰجَكَ ٱلَّٰتِيٓ ءَاتَيۡتَ أُجُورَهُنَّ وَمَا مَلَكَتۡ يَمِينُكَ مِمَّآ أَفَآءَ ٱللَّهُ عَلَيۡكَ وَبَنَاتِ عَمِّكَ وَبَنَاتِ عَمَّٰتِكَ وَبَنَاتِ خَالِكَ وَبَنَاتِ خَٰلَٰتِكَ ٱلَّٰتِي هَاجَرۡنَ مَعَكَ وَٱمۡرَأَةٗ مُّؤۡمِنَةً إِن وَهَبَتۡ نَفۡسَهَا لِلنَّبِيِّ إِنۡ أَرَادَ ٱلنَّبِيُّ أَن يَسۡتَنكِحَهَا خَالِصَةٗ لَّكَ مِن دُونِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَۗ قَدۡ عَلِمۡنَا مَا فَرَضۡنَا عَلَيۡهِمۡ فِيٓ أَزۡوَٰجِهِمۡ وَمَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُهُمۡ لِكَيۡلَا يَكُونَ عَلَيۡكَ حَرَجٞۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورٗا رَّحِيمٗا ﴿٥٠﴾

**50.** አንተ ነብይ ሆይ! እነዚያን መህሮቻቸውን የሰጠሃቸውን ሚስቶችህን፤ አላህ በአንተ ላይ ከመለሰልህም ሴቶች መካከል እነዚያን እጅህ የጨበጠቻቸውን ምርኮኞች ሴቶች፤ እነዚያንም ከአንተ ጋር የተሰደዱትን የአጎቶችህንና፤ የአክስቶችህን ሴት ልጆች (እንደዚሁም) የእናትህ ወንድምና የእናትህ እህት ሴት ልጆች ማግባትን ለአንተ ፈቅደንልሃል። ማንኛዋም በአላህ የአመነች ሴት ራሷን ለነብዩ ብትሰጥ ነብዩ ሊያገባት የፈለገ እንደ ሆነ ከምዕመናን ሌላ ላንተ ብቻ የተሰጠ መብት ሲሆን* ፈቀድንልህ። በምዕመናን ላይ በሚስቶቻቸውና እጆቻቸው በጨበጧቸው ባሮች ነገር ግዴታ ያደረግንባቸውን በእርግጥ አውቀናል። ባንተ ላይ ችግር እንዳይኖር (ያለፉትን ፈቅደንልሃል)። አላህ መሃሪና አዛኝ ነው።

✷ በ (7) ኛው የሂጅራ አመት በዙል-ቀዕዳህ ወር ነብዩና ሁለት ሺህ ሙስሊሞች በሁደይቢያ ስምምነት መሰረት ለሶስት ቀናት ብቻ ተፈቅዶላቸው ወደ መካ ገቡ። መኮች እኒህን የመዲና ወባ ያዳከማቸዉን ሰዎች ተመልከቱ እያሉ ሲያፌዙባቸው ይባስ ብለው አንዳንዶች ሙስሊሞችን ላለማየት ወደ ጋራ ወጡ። በዚህ ምክኒያት ነብዩ (ﷺ) ሙስሊሞች ቀኝ እጃቸውን በማውጣት ሮጥ ሮጥ እያሉ በመሄድ ጥንካሬያቸዉን ለጠላት እንዲያሳዩ አዘዙ።

የሙስሊሞች ጥንካሬ ከሳበቸው ና ካስደሰታቸው ሰዎች መካከል በ (26) ኛ እድሜ ላይ የሚገኙት እናታችን መይሙና ነበሩ። ይቺ ሴት የቀድሞ ባላቸው ሙተውባቸው ነበርና ለእህታቸው ለአባስ ባለቤት ፍላጎታቸዉን በመንገር ራሳቸውን ለነብዩ እንደሰጡ ወሬው በፀባስ በኩል ለነብዩ ደረስና ነብዩም ሀሳቧን ተቀብለው አገቧት። በዚህ ጊዜ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪና፤ አልቢዳያ ወኒሃያ)

**ከአህዛቦች ምዕራፉ ከአንቀፅ (36-50) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ትክክለኛ አማኝ አላህና ነብዩ (ﷺ) በመረጡት ጉዳይ ላይ ምንም አይነት ተቃውሞ ማድረግ እንደሌለበት፤
2. ስለ ዘይድ ኢብኑ ሀሪሳ ትልቅነት፤
3. አላህንና መልዕክተኛውን (ﷺ) ያልታዘዘ ከትክክለኛው መስመር እንዳፈነገጠ፤
4. አላህ ነብዩን እንኳን እንደሚወቅስ፤
5. የነብዩ (ﷺ) አይናፋርነት ምን ያህል ክብደት እንደነበረው፤
6. ከሓዲያንና አመፀኞችን መታዘዝ ክልክል ስለመሆኑ፤
7. ዘይነብ ጉዳይዋን ለአላህ ስትሰጥ በምን መልኩ እንዳነሳትና አላህ ራሱ ለነብዩ (ﷺ) በመዳር የሰጣትን ከፍተኛ ክብር፤
8. አንድን ነገር ለአላህ ብሎ የተወ ሰው አላህ የተሻለ እንደሚሰጠው፤
9. በጃሂሊያ የነበረን የጉዲፈቻን ህግ ማፈራረስ፤
10. ነብዩ (ﷺ) የነብያት ማክተሚያ እንደሆኑ ማረጋገጥ፤
11. አንድን ነገር ለማስተማር ከመናገር አልፎ በተግባር ማሳየት ከፍተኛ የማስተማሪያ ዘዴ መሆኑን፤
12. ነብዩ (ﷺ) የተላኩበትን ነገር በሙሉ እንዳስተማሩና የሚደብቁት ነገር ቢኖር ኖሮ የተወቀሱበትን ነገር ይደበቁ እንደነበር፤
13. በትዳር ላይ ያለች ሴት ሳትፈታ ለሌላ ትዳር መደራደር ክልክል እንደሆነ፤
14. ሚስትን ሊፈታ ያማከረ ሰው በተቻለ ያህል እንዳይፈታ መምከር እንደሚገባ፤
15. አላህን ጧት ማታ ማውሳት እንደሚገባ፤
16. አላህ ለምእመናን የሰጠው ችሮታ፤
17. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
18. ትክክለኛ አማኝን በጀነት ማብሰር፤
19. የነብዩን (ﷺ) ሙሉዕነት በግልፅ ማሳየት፤
20. የኒካህ ህግን ማፅደቅ፤
21. ከግብረስጋ ግንኙነት በፊት መፋታት እንደሚቻል፤ በዚህ መልኩ የተፈታች ሴት ኢዳህ መቁጠር እንደሌለባት፤
22. የተፈታች ሴት መህሯ ቀድሞ ካልተወሰነ ቃዲው በሚወስነው መሰረት የሞራል መጠበቂያ መስጠት ግዴታ መሆኑን፤
23. የተፋታችን ሴት በምንም ነገር ማስቸገር ተገቢ እንዳልሆነ፤
24. ከአራት በላይ ማግባት እንደሚችሉ ለነብዩ መደንገጉ፤
25. የአላህ ርህራሄና እዝነት ምን ያህል ሰፊ እንደሆነ እንማራለን።

۞ تُرۡجِي مَن تَشَآءُ مِنۡهُنَّ وَتُـٔۡوِيٓ إِلَيۡكَ مَن تَشَآءُۖ وَمَنِ ٱبۡتَغَيۡتَ مِمَّنۡ عَزَلۡتَ فَلَا جُنَاحَ
عَلَيۡكَۚ ذَٰلِكَ أَدۡنَىٰٓ أَن تَقَرَّ أَعۡيُنُهُنَّ وَلَا يَحۡزَنَّ وَيَرۡضَيۡنَ بِمَآ ءَاتَيۡتَهُنَّ كُلُّهُنَّۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ مَا
فِي قُلُوبِكُمۡۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَلِيمٗا ٥١

**51.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ መካከል የምትፈልጋትን ታቆያለህ። የምትፈልጋትንም ወደ አንተ ታስጠጋለህ። በመፍታት ከአራቅሃትም የፈለግሃትን በመመለስ ብታስጠጋ በአንተ ላይ ኃጢአት የለብህም። ይህ ዓይኖቻቸው መርጋት ወደ አለማዘናቸውም ለሁሉም በሰጠሃቸው ነገር ወደ መውደዳቸውም በጣም የቀረበ ነው። አላህም በልቦቻችሁ ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል። አላህ አዋቂና ታጋሽ ነው።

لَّا يَحِلُّ لَكَ ٱلنِّسَآءُ مِنۢ بَعۡدُ وَلَآ أَن تَبَدَّلَ بِهِنَّ مِنۡ أَزۡوَٰجٖ وَلَوۡ أَعۡجَبَكَ حُسۡنُهُنَّ
إِلَّا مَا مَلَكَتۡ يَمِينُكَۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ رَّقِيبٗا ٥٢

**52.** ከእነዚህ በኋላ እጅህ ከጨበጠቻቸው ባሮች በስተቀር ሴቶች ለአንተ አይፈቅዱልህም ከሚስቶችም መልካቸው ቢደንቅህም እንኳን በእነርሱ ልትለውጥ አይፈቀዱልህም አላህ በነገሩ ሁሉ ተጠባባቂ ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَدۡخُلُواْ بُيُوتَ ٱلنَّبِيِّ إِلَّآ أَن يُؤۡذَنَ لَكُمۡ إِلَىٰ طَعَامٍ غَيۡرَ نَٰظِرِينَ
إِنَىٰهُ وَلَٰكِنۡ إِذَا دُعِيتُمۡ فَٱدۡخُلُواْ فَإِذَا طَعِمۡتُمۡ فَٱنتَشِرُواْ وَلَا مُسۡتَـٔۡنِسِينَ لِحَدِيثٍۚ إِنَّ
ذَٰلِكُمۡ كَانَ يُؤۡذِي ٱلنَّبِيَّ فَيَسۡتَحۡيِۦ مِنكُمۡۖ وَٱللَّهُ لَا يَسۡتَحۡيِۦ مِنَ ٱلۡحَقِّۚ وَإِذَا سَأَلۡتُمُوهُنَّ
مَتَٰعٗا فَسۡـَٔلُوهُنَّ مِن وَرَآءِ حِجَابٖۚ ذَٰلِكُمۡ أَطۡهَرُ لِقُلُوبِكُمۡ وَقُلُوبِهِنَّۚ وَمَا كَانَ لَكُمۡ أَن
تُؤۡذُواْ رَسُولَ ٱللَّهِ وَلَآ أَن تَنكِحُوٓاْ أَزۡوَٰجَهُۥ مِنۢ بَعۡدِهِۦٓ أَبَدًاۚ إِنَّ ذَٰلِكُمۡ كَانَ عِندَ ٱللَّهِ
عَظِيمًا ٥٣ إِن تُبۡدُواْ شَيۡـًٔا أَوۡ تُخۡفُوهُ فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٗا ٥٤

**53-54.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ መድረሱን የማትጠባበቁ ስትሆኑ ወደ ምግብ ካልተፈቀደላችሁ በስተቀር የነብዩን ቤቶች በምንም ጊዜ አትግቡ ግን በተጠራችሁ ጊዜ ግቡ በተመገባችሁም ጊዜ ወዲያውኑ ተበተኑ። ለወግ የምትጫወቱ ሆናችሁም አትቆዩ። ይሄችሁ ነብዩን በእርግጥ ያስቸግራል። ከናንተም ያፍራል ግን አላህ ከእውነት አያፍርም። እቃንም ለመዋስ በጠየቃችኋቸው ጊዜ ከመጋረጃ ኋላ ሆናችሁ ጠይቋቸው ይሄችሁ ለልቦቻችሁ

ለልቦቻቸውም የበለጠ ንጽህና ነው፡፡ የአላህንም መልክተኛ ልታስቸግሩ ሚስቶቹንም ከእርሱ በኋላ ምንጊዜም ልታገቡ ለእናንተ አይገባችሁም ይሃችን አላህ ዘንድ ከባድ ኃጢአት ነው፡፡ ማንኛውንም ነገር ብትገልፁ ወይም ብትደብቁት በእርሱ ይመነዳችኋል፡፡ አላህ ነገሩን ሁሉ አዋቂ ነውና፡፡

لَّا جُنَاحَ عَلَيْهِنَّ فِيٓ ءَابَآئِهِنَّ وَلَآ أَبْنَآئِهِنَّ وَلَآ إِخْوَٰنِهِنَّ وَلَآ أَبْنَآءِ إِخْوَٰنِهِنَّ وَلَآ أَبْنَآءِ أَخَوَٰتِهِنَّ وَلَا نِسَآئِهِنَّ وَلَا مَا مَلَكَتْ أَيْمَٰنُهُنَّۗ وَٱتَّقِينَ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٖ شَهِيدًا ﴿٥٥﴾

**55.** (የነብዩ ሚስቶች) በአባቶቻቸው በወንዶች ልጆቻቸውም በወንድሞቻቸውም በወንድሞቻቸው ወንዶች ልጆችም በእህቶቻቸው ወንዶች ልጆችም ምዕመናት በሆኑት በሴቶቻቸውም በጨበጧቸውም ባሮች አጠገብ ቢገለጡ በእነርሱ ላይ ኃጢአት የለባቸውም፡፡ ሴቶች ሆይ! ታዘዙ፡፡ አላህን ፍሩ፡፡ አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ መስካሪ ነውና፡፡

**ከአህዛብ ምዕራፉ ከአንቀፅ (51-55) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ለነብዩ (ﷺ) ነገሮችን በማግራት የዋለላቸውን ውለታ፤
2. ለነብዩ (ﷺ) የተፈቀደ ለሌላ አማኝ ግን ያልተፈቀደ ነገር እንዳለ፤
3. አላህ ለነብዩ (ﷺ) ና ለባለቤቶቻቸው ያዘጋጀው ነገር በማንም ተቆጥሮ የማያልቅ መሆኑ፤
4. ለአላህ ብሎ አንድ ነገር የተወ ሰው በተሻለ ነገር እንደሚክሰው፤
5. ሁልጊዜም አላህን መጠባበቅ ግዴታ ስለመሆኑ፤
6. ለምግብም ሆነ ለሌላ ወደ ቤት ሲገባ አስፈቅዶ መሆን እንዳለበት፤
7. ነብዩ (ﷺ) የነበራቸውን አይናፋርነት በግልፅ ማሳየት፤
8. አላህ ሀቅን ከመናገር ወደኋላ እንደማይል፤
9. ባዕድ ወንድና ሴት ከመጋረጃ በስተጀርባ መነጋገር እንደሚችሉ፤
10. ነብዩን (ﷺ) ማስቸገር ከታላላቅ ወንጀሎች መሆኑን፤
11. ሴትን ያናገረ ወይም የተመለከተ ከችግር እንደማይድን ወይም እንደማይጠራ፤
12. የነብዩን (ﷺ) ሚስቶች ማግባት የተከለከለ ስለመሆኑ፤
13. የሴት ልጅ ዘመዶች እነማን እንደሆኑ መግለፅ፤
14. አላህን መፍራት ተገቢ ስለመሆኑ እንማራለን፡፡

إِنَّ ٱللَّهَ وَمَلَٰٓئِكَتَهُۥ يُصَلُّونَ عَلَى ٱلنَّبِيِّۚ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ صَلُّواْ عَلَيْهِ وَسَلِّمُواْ تَسْلِيمًا ﴿٥٦﴾

**56.** አላህና መላዕክቱ በነብዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ፡፡ እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፡፡ የማክበርን ሰላምታንም ሰላም በሉ፡፡*

✷ ከአህዛብ ምዕራፍ (56) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ሙስሊሞች ወደ ነብዩ መሐመድ (ﷺ) መጥተው በእርስዎ ላይ ሰላም እንዴት እንደምንል አውቀናል ስለዋትስ እንዴት እንበል ብለው ስለ ጠየቋቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

✷ ለነብዩ ሶለዋት ማውረድ ከፍተኛ ምንዳ አለው። ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች የተወሱት ናቸው።

1. ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አብዱረህማን ኢብኑ አቢ ለይላ እንዳስተላለፉት፤ ከዕብ ኢብኑ ዑጅራህ አገኘኝና «ከነብዩ (ﷺ) የሰማሁትን አንድ ስጦታ ልስጥህ?» አለኝ። እኔም «እንዴታ!» አልኩት። እሱም «የአላህ መልዕክተኛ በእርሰዎ ላይ ሰላምታ እንዴት እንደምናቀርብ አላህ አስተምሮናል። ታዲያ በእርስዎ ቤተሰነብ ላይ እንዴት ነው ሰላምታ የምናቀርበው? ስንል ጠየቅናቸው። እሳቸውም «ጌታችን ሆይ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትን እንዳወረድከው በሙሐመድና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትን አውርድ። አንተ በእርግጥ እጅጉን የተመሰገንክና የላቅክ ነህ። አሉን።»
2. ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ ኢብኑ ዐምር ኢብኑ አልዓስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተከታዩን ሲናሩ ሰምቻለሁ በማለት አስተላልፈዋል፦ «በኔ ላይ አንድ ጊዜ ያወረደ አላህ በርሱ ላይ አስር ሶላቶችን ያወርድለታል።»
3. ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ «በዕለተ ቂያማ ለኔ ይበልጥ የተገባው ሰው በኔ ላይ አብዝቶ ሶላት ያወረደ ነው።»
4. አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ አውስ ኢብኑ አውስ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ «ከቀኖቻችሁ ሁሉ በላጩ የጁመዓ ቀን ነው። ጁመዓ ቀን በኔ ላይ ሶላት አብዙ። ሶላዋቶቻችሁ ይቀረቡልኛል» አሉ። ባልደረቦቻቸውም፦ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አካሎዎ በአፈር ተበልቶ እያለ እንዴት ነው የኛ ሶላዋት የሚቀርብዎ» በማለት ጠየቋቸው። እርሳቸውም፦ «በምድር የነብያትን አካል እንዳትበላ አላህ ከልክሏል» አሉ።
5. ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ከአጠገቡ ተወስቼ በኔ ላይ ሶለዋት ያላዋረደ ሰው ከሰረ።»
6. ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፦ «ለኔ ሰላምታ የሚያቀርብልኝ አንድም ሰው የለም አላህ ነፍሴን በመመለስ ለሰላምታው መልስ እንደሰጥ የሚያደርገኝ ቢሆን እንጂ»
7. ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ዐሊይ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ስስታም ማለት ከአጠገቡ ተወስቼ በኔ ላይ ሶለዋት ያላወረደ ነው።»
8. ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሙሐመድ ከዕብ ዑጅረህ እንዳስተላለፉት፦ ነብዩ ወደኛ መጡ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለርስዎ እንዴት ሰላምታ ማቅረብ እንዳለብን አወቅን። ሶለዋት የምናወርደውስ እንዴት ነው?» በማለት ጠየቅናቸው። እንዲህ እንድል አስተማሩን፦ «አልላሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አሊ ሙሐምመደን ከማ ሶልለይተ ዐላ አሊ ኢብራሂይመ ኢንከ ሐሚይዱን መጂይድ። አልላሁምመ ባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ አሊ ሙሐመዲን ከማ ባረክተ ዐላ አሊ ኢብራሂመ ኢነከ ሐሚይዱን መጂይድ።
9. ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ መስዑድ አል. አድሪይ እንዲህ ሲሉ አስተላለፈዋል፦ ከሰዕድ ኢብኑ ዐብደላህ ዘንድ ተቀምጠን እያለ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) መጡ። «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ በርስዎ ላይ ሰለዋት እንድናወርድ አዞናል። እንዴት ነው የምናወርደው?» ሲል በሺር እብ ሰዕድ ጠየቃቸው። ባልጠየቃቸው ጥሩ ነበር ብለን እስከ ምንመኝ ድረስ ዝም አሉ። ከዚያም እንዲህ አሉ። «አልላሁምም ሶልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አሊ ሙሐመዲን ከማ ሶልሊ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ አሊ ሙሐመዲን ከማ ሶልለዬተ ዐላ አሊ ኢብራሂይመ እንነከ ሐሚይዱን መጂይድ፤ በሉ። ሰላምታ እንዴት እንደምታቀርቡልኝ ታውቃላችሁ።»
10. አቡ ሑመይድ አስ. ሰዒዳይ እንዳስተላፉት «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በርስዎ ላይ ሰለዋት የምናወርደው እንዴት ነው በማለት ሰዎች ጠየቋቸው። እርሳቸውም እንዲህ እንዲሉ

አስተማሯቸው፡- «አልሏሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አዝዋጂሂ ወዙሪይየቲሂ ከማ ሶልለይተ ዐላ አሊ ኢብራሂይመ ወባረክ ዐላ ሙሐምመድን ወዐላ አዝዋጂሂ ወዙሪይየቲሂ ከማ ባረከተ በላ አሊ ኢብራሂይመ ኢንነከ ሐሚይዱን መጂይድ።»

በመሆኑም ሶለዋት መለመን ሁልዜም ተፈላጊ ቢሆንም ጁሙዓ ቀንና ሌሊቱ ላይ በጣም ይወደዳል። ስማቸው በተወሳ ቁጥር ም እንዲሁ ይወደዳል። አነጦሓዊና ሌሎችም ስማቸው በተወሳ ቁጥር ግዴታ ነው ብለዋል። በየሶላቱ በመጨረሻው ተሸሁድ ላይ፤ በጁሙዓና በዒድ ኹጥባ ዉስጥ ግዴታ ነው የሚሉት ብዙ ናቸው። ኢብኑል ቀይም ጃላኡል አፍሃም በተባለው መፅሐፍ ሶለዋት መለመን አርባ ቦታ ላይ ይገባል ብለው ዘርዝረውታል። ከፋይዳዎችም አርባ ጥቅሞችን ዘርዝረዋል።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُؤْذُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ لَعَنَهُمُ ٱللَّهُ فِي ٱلدُّنْيَا وَٱلْأَخِرَةِ وَأَعَدَّ لَهُمْ عَذَابًا مُّهِينًا ﴿٥٧﴾
وَٱلَّذِينَ يُؤْذُونَ ٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتِ بِغَيْرِ مَا ٱكْتَسَبُواْ فَقَدِ ٱحْتَمَلُواْ بُهْتَٰنًا وَإِثْمًا مُّبِينًا ﴿٥٨﴾

**57-58.** እነዚያ አላህንና መልክተኛውን የሚያስከፉ በቅርቢቱ ዓለምም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም አላህ ረግሟቸዋል። ለእነርሱም አዋራጅን ቅጣት ደግሶላቸዋል። እነዚያም ምዕመናንና ምዕመናትን ባልሰሩት ነገር በመዝለፍ የሚያሰቃዩ ዕብለትንና ግልፅ ኃጢአትን በእርግጥ ተሸከሙ።*

* ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሙስሊምን መሳደብ በአላህ ትዕዛዝ ላይ ማመፅ ሲሆን መጋደል ደግሞ ክህደት ነው።»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተከታዩን ሲናገሩ እንደሰሙ አቡ ዘር አስተላልፈዋል፡- «አንድን ሰው ሌላኛውን በአመፅ ወይም በክህደት ከሰደበው ሰውየው ለዚህ ለስድቡ ተገቢ ሆኖ ካልተገኘ ስድቡ ወደርሱ ይመለስበታል»

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የሚሰዳደቡ ሰዎች የሚሸምቱት የስድብ ኃጢአት ተበዳዩ ድንበር እስካለፈ ድረስ በጀማሪ ላይ ይጫናል።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተከታዩን ሲናገሩ ሰምቻለሁ በማለት አቡ ሁረይራ አስተላልፈዋል፡- «አገልጋዩን በዝሙት የሰደበ እርሱ እንዳለው ሆኖ ካልተገኘ በዕለተ ቂያማ የዝሙት ቅጣት ይፈፀምበታል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሙታንን አትሳደቡ። እነርሱ ወዳስቀደሙት ተግባር ደርሰዋልና።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ሙስሊም ማለት ሙስሊሞች ከምላሱም ሆነ ከእጁ ሰላም የሆነለት ሰው ነው። ስደተኛ ማለት አላህ ከከለከለው የተሰደደ ነው።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አትጣሉ፤ አትመቀኛኙ፤ አትኮራረፉ፤ አትቆራረጡ። ወንድማማቾች የሆናችሁ የአላህ ባሮች ሁኑ። ሙስሊም ወንድሙን ከሶስት ቀን በላይ ሊያኮርፈው አይፈቀድለትም።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የጀነት በሮች ሰኞና ሐሙስ ይከፈታሉ። በአላህ ላይ ላላጋሩ ሰዎች ሁሉም ምህረት ይለገሳል። በርሱና በወንድሙ መካከል ጥል ያለበት ሰው ሲቀር። ለጠበኞች ግን «እነዚህን እስኪታረቁ ድረስ ተዋቸው» ይባላሉ።»

በሌላ ዘገባ «ዘወትር ሐሙስና ሰኞ ስራዎች ይቀርባሉ» የሚል ተወስቷል። አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እ ንዲህ ብለዋል፡- «ምቀኝነትን ተጠንቀቅ። እሳት እንጨትን እንደምትበላው ምቀኝነትም መልካም ስራዎችን ይበላል»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ጥርጣሬን ተጠንቀቁ። ጥርጣሬ ከወሬዎች ሁሉ የከፋ ሐሰተኛ ወሬ ነውና። ነውርን አትከታተሉ። አትሰልሉ። የሌሎችን ድርሻ ለመውሰድ አትሽቀዳደሙ። አትመቀኛኙ። አትጣሉ። አትቀያየሙ። አላህ እንዳዘዛችሁ ወንድማማቾች የሆናችሁ የአላህ ባሮች ሁኑ። ሙስሊም የሙስሊም ወንድም ነው። አይበድለውም፤ አጋጦ አይተወውም፤ አይናቀውም» አሉና እጃቸውን ወደ ደረታቸው እያመላቱ«አላህን መፍራት እዚህ ውስጥ ነው» አሉ። በመቀጠልም እንዲህ አሉ፡- «አንድ ሰው ሙስሊም ወንድሙን መናቁ ብቻ ከክፉ ድርጊት በቂው ነው። የእያንዳንዱ ሙስሊም ደም፤ ክብርና ገንዘብ በሙስሊሞች ላይ እርም ነው። አላህ የሚመለከተው አካላችሁን ወይም ላያዊ ገፅታችሁን ሳይሆን ተግባራችን እና ልቦናችሁን ነው»

በሌላ ዘገባ «አትቆራረጡ፤ አትቀያየሙ፤ አትጠላሉ፤ አትመቀኛኙ። ወንድማማቾች የሆናችሁ የአላህ ባሮች ሁኑ።»

በሌላ ዘገባ፡- «አትኮራረፉ፤ አንዳችሁ በሌላኛችሁ ሽያጭ ላይ አይሽጥ» የሚል ሰፍሯል።

አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላለፉት አንድ ሰው ከጺሙ ላይ አስካሪ መጠጥ እየተንጠባጠበ ከርሳቸው ዘንድ ቀረበ። «እንዳንሰልል ተከልክለናል። በግለልፅ ያየነውን ግን እንቀበላለን» አሉ።

ከአህዛብ (57) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ መሐመድ (ﷺ) እናታችን ሶፊያን ባገቡ ጊዜ በነበረው አሉባልታ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

ከአህዛብ ምዕራፍ (58) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንዶች አንዲት የአንሷር ሴት ተገልጣ ስትሄድ ዑመር አይተዋት ስለመቷት ለቤተሰቦቸዋ ሄዳ ነገረችና ዘመዶቿ ዑመርን ስላሰቃዩዋቸው ነው የወረደው ሲሉ ሌሎች ደግሞ አስመሳዮች ዓልይን መከራ ያሳይዋቸው ስለነበር ብለዋል። (ዋሒዲ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ قُل لِّأَزۡوَٰجِكَ وَبَنَاتِكَ وَنِسَآءِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ يُدۡنِينَ عَلَيۡهِنَّ مِن جَلَٰبِيبِهِنَّۚ ذَٰلِكَ أَدۡنَىٰٓ أَن يُعۡرَفۡنَ فَلَا يُؤۡذَيۡنَۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورٗا رَّحِيمٗا ﴿٥٩﴾

**59.** አንተ ነብይ ሆይ! ለሚስቶችህ ለሴቶች ልጆችህም ለምእመናን ሚስቶችም ከመከናነቢያዎቻቸው በላያቸው ላይ እንዲለቁ ንገራቸው ይህ እንዳይታወቁና በባለጌዎች እንዳይደፈሩ ለመሆን በጣም የቀረበ ነው። አላህ መሃሪና አዛኝ ነውና።

ከአህዛብ ምዕራፍ (59) ኛው አንቀፅ ወደረበት ምክንያት፡- የነብዩ መሐመድ (ﷺ) ባለቤት የነበሩት ሰውዳህ ቢንቱ ዘምዓህ ወፍራምና ሐጃብ ከወረደም በኋላ ከልብሳቸው በላይም የሚለዩ ስለነበሩ ከሒጃብ በኋላ ከዕለታት አንድ ቀን ለግል ጉዳያቸው ሲወጡ ዑመር አይተዋቸው «ሰውዳህ እንዴት መውጣት እንዳለብሽ ብታስቢበት መልካም ይመስለኛል። ማንነትሽ አይጠፋንም» ሲሏት ወዲያው ተመልሳ ለነብዩ መሐመድ ስለነገረቻቸው ወዲያውኑ እነዚህ አናቅፅ ወረዱ። (ሱዩጢ)

۞ لَّئِن لَّمْ يَنتَهِ ٱلْمُنَٰفِقُونَ وَٱلَّذِينَ فِى قُلُوبِهِم مَّرَضٌ وَٱلْمُرْجِفُونَ فِى ٱلْمَدِينَةِ لَنُغْرِيَنَّكَ
بِهِمْ ثُمَّ لَا يُجَاوِرُونَكَ فِيهَآ إِلَّا قَلِيلًا ﴿٦٠﴾ مَّلْعُونِينَ ۖ أَيْنَمَا ثُقِفُوٓا۟ أُخِذُوا۟ وَقُتِّلُوا۟ تَقْتِيلًا ﴿٦١﴾
سُنَّةَ ٱللَّهِ فِى ٱلَّذِينَ خَلَوْا۟ مِن قَبْلُ ۖ وَلَن تَجِدَ لِسُنَّةِ ٱللَّهِ تَبْدِيلًا ﴿٦٢﴾

**60-62.** መናፍቃንና እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ (የአመንዝራነት) በሽታ ያለባቸው በመዲናም ውስጥ (በወሬ) አሸባሪዎቹ ከዚህ ስራቸው ባይከለከሉ በእርሱ ላይ በእርግጥ እንቀሰቅስሃለን ከዚያ በእርሷ ውስጥ ጥቂትን እንጂ አይጎራበቱህም። የተረገሙ ሆነው እንጂ (አይጎራበቱህም)። በየትም ስፍራ ቢገኙ ይያዛሉ። መገደልንም ይገደላሉ። እነዚህ ህጎች በእነዚያ ከዚህ በፊት ባለፉት ህዝቦች ላይ የደነገጋቸው የአላህ ድንጋጌ ናቸው። ለአላህ ድንጋጌዎች ደግሞ ፈጽሞ መለወጥን አታገኝም።

يَسْـَٔلُكَ ٱلنَّاسُ عَنِ ٱلسَّاعَةِ ۖ قُلْ إِنَّمَا عِلْمُهَا عِندَ ٱللَّهِ ۚ
وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّ ٱلسَّاعَةَ تَكُونُ قَرِيبًا ﴿٦٣﴾

**63.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰዎች ከሰዓቲቱ ይጠይቁሃል። እውቀትዋ አላህ ዘንድ ብቻ ነው በላቸው። የሚያሳውቅህም ምንድን ነው፣ ሰዓቲቱ በቅርብ ጊዜ ልትሆን ይከጀላል።

إِنَّ ٱللَّهَ لَعَنَ ٱلْكَٰفِرِينَ وَأَعَدَّ لَهُمْ سَعِيرًا ﴿٦٤﴾ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًا ۖ لَّا يَجِدُونَ وَلِيًّا
وَلَا نَصِيرًا ﴿٦٥﴾ يَوْمَ تُقَلَّبُ وُجُوهُهُمْ فِى ٱلنَّارِ يَقُولُونَ يَٰلَيْتَنَآ أَطَعْنَا ٱللَّهَ وَأَطَعْنَا
ٱلرَّسُولَا۠ ﴿٦٦﴾ وَقَالُوا۟ رَبَّنَآ إِنَّآ أَطَعْنَا سَادَتَنَا وَكُبَرَآءَنَا فَأَضَلُّونَا ٱلسَّبِيلَا۠ ﴿٦٧﴾
رَبَّنَآ ءَاتِهِمْ ضِعْفَيْنِ مِنَ ٱلْعَذَابِ وَٱلْعَنْهُمْ لَعْنًا كَبِيرًا ﴿٦٨﴾

**64-68.** አላህ ከሓዲያንን በእርግጥ ረግሟቸዋል ለነርሱም የተጋጋመችን እሳት አዘጋጅቷል። በእርሷ ውስጥ ዘለዓለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ ወዳጅም ረዳትም አያገኙም። ፊቶቻቸው በእሳት ውስጥ በሚገለባበጡ ቀን ዋ ምኞታችን አላህን በተገዛን መልክተኛውንም በታዘዝን ኖሮ እያሉ ይፀፀታሉ። ይላሉም ጌታችን ሆይ! እኛ ጌቶቻችንንና ታላላቆቻችንን ታዘዝን መንገዱንም አሳሳቱን። ጌታችን ሆይ! ከቅጣቱ እጥፍን ስጣቸው ታላቅን እርግማንንም እርገማቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَكُونُواْ كَٱلَّذِينَ ءَاذَوۡاْ مُوسَىٰ فَبَرَّأَهُ ٱللَّهُ مِمَّا قَالُواْۚ وَكَانَ عِندَ ٱللَّهِ وَجِيهٗا ٦٩

**69.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ እንደ እነዚያ ሙሳን እንዳሰቃዩት*1 ሰዎች አትሁኑ ካሉትም ነገር ሁሉ አላህ አጠራው።*2 ከአላህም ዘንድ ባለሞገስ ነበር።

*1 በቁርዓን ከተነገሩት ውስጥ ለምሳሌ የኢስራኤል ልጆች ሆይ! ሙሳ ሆይ! «በአንድ ዓይነት ምግብ ላይ በፍፁም አንታገስም። ስለዚህ ጌታህ ከእነዚያ ምድር ከምታበቅላቸው ከቅጠላ ቅጠሏ፤ ከዱባዋ፤ ከስንዴዋ፤ ከምስሯና ከሽንኩርቷ ያወጣልን ዘንድ ለምንል» ባሏቸው ጊዜ የሆነውን ታሪክ አስታውሱ። ሙሳ ያንን ዝቅተኛ የሆነውን በዚያ ከፍተኛና በላጭ በሆነው ነገር ልትተኩ ትፈልጋላችሁን? ወደ ከተማ ውረዱ። ለእናንተም የጠየቃችሁትን ነገር ታገኛላችሁ አላቸው። በውርደትና በድህነት ተንገላቱ። የአላህ ቁጣ ሰፈነባቸው። ይህ እነርሱ በአላህ ተዐምራትና መፅሐፍ ይክዱና ነብያትንም ያለ አግባብ ይገድሉ ስለነበሩ ኃጢአት ላይ በመዘፈቃቸውና እንዲሁም ወሰን የሚያልፉ በመሆናቸው ነው።

ሙሳ ሆይ! የአላህን ተፈጥሮ (መጥመቅ) (መንከር) እምነት ያዙ በመንከርም ከአላህ ይበልጥ ያመረ ማነው? (ማንም የለም)። እኛም ለእርሱ ብቻ ተገዢዎች ነን በሉ።

ሙሳ ሆይ! አላህን በይፋ እስከምናይ ድረስ ለአንተ በፍፁም አናምንልህም ባሏቸው ጊዜ የሆነውን ታሪክ አስታውስ። እናንተም እየተመለከታችሁ መብረቅ መታችሁ» የሚሉት ይገኙበታል።

*2 በሙሳ ላይ ካደረሷቸው ስቃዮች መካከል ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ሙሳ እጅግ በጣም ዓይናፋርና ጥብቅ ከመሆናቸው የተነሳ አንዲት የቆዳቸው ክፍል አይታይም ነበር። በአንድ ወቅት ከኢስራኤል ልጆች መካከል አንዱ «በቆዳው ላይ አንዳች ነውር ማለትም ለምጥ ወይም ቁምጥና ወይም ሌላ ነገር ከሌለበት በስተቀር እንዲህ አይሸፋፈንም ነበር።» ሲል በነገር ተነኮሳቸው። አላህም ከዚህ አይነቱ ተንኮል ሙሳን ለማፅዳት ፈለገ። ስለዚህም አንድ ቀን ሙሳ ከሰዎች እይታ ርቀው ብቻቸውን ሆኑና ልብሳቸውን አውልቀው ድንጋይ ላይ አስቀመጡና ገላቸውን ታጥበው ከጨረሹ በኋላ ልብሱን ከድንጋይ ላይ ለማንሳት ሲሉ ድንጋዩ ልብሱን ይዞ ወደታች ወረደ። ሙሳ በትራቸውን ይዘው ከድንጋዩ ኋላ «ድንጋዩን በብትሩ ሲመቱት በአላህ እምላለሁ ድንጋዩ በብትሩ ምት ወደ ሶስት ወይም አራት ወይም አምስት ቦታ ተፈረካከሰ ይህም «እናንተ ያመናችሁ ሆይ! እንደነዚያ ሙሳን እንዳሳቃዩት ሰዎች አትሁኑ፤ ካሉትም ነገር ሁሉ አላህ አጠራው፤ አላህም ዘንድ ባለሞገስ ነበር።» (አል አሕዛብ፡ 69) ያለው ነው።»

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَقُولُواْ قَوۡلٗا سَدِيدٗا ٧٠ يُصۡلِحۡ لَكُمۡ أَعۡمَٰلَكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡۗ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَقَدۡ فَازَ فَوۡزًا عَظِيمًا ٧١

**70-71.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህን ፍሩ። ትክክለኛን ንግግርም ተናገሩ። ስራዎቻችሁን ለእናንተ ያበጅላችኋልና ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምርላችኋል። አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዝም ሰው ሁሉ በእርግጥ ታላቅን እድል አገኘ።

إِنَّا عَرَضۡنَا ٱلۡأَمَانَةَ عَلَى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَٱلۡجِبَالِ فَأَبَيۡنَ أَن يَحۡمِلۡنَهَا وَأَشۡفَقۡنَ مِنۡهَا
وَحَمَلَهَا ٱلۡإِنسَٰنُۖ إِنَّهُۥ كَانَ ظَلُومٗا جَهُولٗا ٧٢

72. እኛ አደራን በሰማያት በምድር እና በተራራዎች ላይ አቀረብናት፡፡ መሸከሟንም እንቢ አሉ ከእርሷም ፈሩ ሰው ግን ተሸከማት እርሱ በጣም በደለኛና ተሳሳች ነውና፡፡

لِّيُعَذِّبَ ٱللَّهُ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ وَٱلۡمُنَٰفِقَٰتِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ وَٱلۡمُشۡرِكَٰتِ وَيَتُوبَ ٱللَّهُ عَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ
وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۗ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورٗا رَّحِيمَۢا ٧٣

73. ወንዶች መናፍቃንንና ሴቶች መናፍቃትን ወንዶች አጋሪዎችንና ሴቶች አጋሪዎችም አላህ ሊቀጣ በምዕምናንና በምዕመናትም ላይ አላህ ንስሃን ሊቀበል አደራዋን ሰው ተሸከማት፡፡ አላህ መሃሪና አዛኝ ነውና፡፡

**ከአህዛቦች ምዕራፍ ከአንቀፅ (68-73) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ አስመሳዮች ንሰሀ ካልገቡ የተለመደው እርምጃ እንደሚፈፅምባቸው መዛቱን፤
2. ወንጀለኞችን ከጥፋታቸው እስከሚመለሱ ድረስ ማራቅ ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. የትንሳኤ ቀን መች እንደሆነ ያለ አላህ ማንም እንደማያውቀው፤
4. የትንሳኤ ዕለት ቅርብ እንደሆነና አርቀን መመልከት እንደሌለብን፤
5. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
6. ጭፍን ተከታይነት ለከፋ አደጋ እንደሚያጋልጥ፤
7. ወንጀልን ለመስራት አለቆችን መስማትና እነርሱን መታዘዝ መጨረሻው አደገኛ እንደሆነ
8. አላህን መፍራት ግዴታ ስለ መሆኑ፤
9. መልካም ስራ ውጤቱ በዚህች ዓለምም እንደሚበጅ፤
10. አላህንና ነብዩን (ﷺ) መታዘዝ በሁለቱም ዓለም የደስታና የስኬት ምንጭ ስለ መሆኑ፤
11. አደራ መጠበቅና በተገቢው ማድረስ ግዴታ መሆኑን፤
12. የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊ መስመር ከሳተ ለራሱ እንኳን የሚጠቅመውን ለይቶ የማያውቅ ግፈኛና ደንቆሮ መሆኑን እንማራለን፡፡

በአላህ ፈቃድ የአህዛቦች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ፡፡

# ምዕራፍ (34)
# የሰበእ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ሰበእ)

سُورَةُ سَبَإٍ

በመካ የወረደ ምእራፍ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (54) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِي لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَهُ ٱلۡحَمۡدُ فِي ٱلۡأٓخِرَةِۚ
وَهُوَ ٱلۡحَكِيمُ ٱلۡخَبِيرُ ١

**1.** ምስጋና ሁሉ ለዚያ በሰማያት ያለው በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይገባው። በመጨረሻይቱም ዓለም ምስጋና ሁሉ ለእርሱ ብቻ ነው። እርሱም ብልሃተኛና (ጥበበኛ) ውስጠ አዋቂው ነው።

يَعۡلَمُ مَا يَلِجُ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا يَخۡرُجُ مِنۡهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ وَمَا يَعۡرُجُ فِيهَاۚ
وَهُوَ ٱلرَّحِيمُ ٱلۡغَفُورُ ٢

**2.** አላህ በምድር ውስጥ የሚገባውን ሁሉ ከእርሷ የሚወጣውን ከሰማይም የሚወርደውን በእሷ ውስጥ የሚያርገውን ሁሉ ያውቃል። እርሱም አዛኝና መሃሪ ነው።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَا تَأۡتِينَا ٱلسَّاعَةُۖ قُلۡ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتَأۡتِيَنَّكُمۡ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِۖ لَا يَعۡزُبُ
عَنۡهُ مِثۡقَالُ ذَرَّةٖ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَلَآ أَصۡغَرُ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكۡبَرُ إِلَّا فِي
كِتَٰبٖ مُّبِينٖ ٣ لِّيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِۚ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَرِزۡقٞ
كَرِيمٞ ٤ وَٱلَّذِينَ سَعَوۡ فِيٓ ءَايَٰتِنَا مُعَٰجِزِينَ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ عَذَابٞ مِّن رِّجۡزٍ أَلِيمٞ ٥

**3-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱትም ሰዎች ሰዓቲቱ አትመጣብንም አሉ፡ ጉዳዩ እንዳሰባችሁት አይደለም በላቸው። ሩቁን ሁሉ

አዋቂ በሆነው ጌታዬ እምላለሁ። በእርግጥ ትመጣባችኋለች። የብናኝ ክብደት ያክል እንኳ በሰማያትና በምድር ውስጥ ከእሱ አይሰወርም አይርቅም። ከዚህ ያነሰም ሆነ የበለጠ የለም በግልጹ መጽሐፍ ውስጥ የተመዘገበ ቢሆን እንጂ። እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሰሩትን ሊመነዳ (ሰአቲቱ ትመጣባችኋለች) እነዚያ ለእነርሱ ምህረትና የከበረ ሲሳይ አለባቸው። እነዚያም የሚያመልጡ መስሏቸው አንቀፆቻችንን ለማፍረስ የጣሩ እነዚያ ለእነርሱ ከመጥፎ ቅጣት የሆነ አሳማሚ ስቃይ አለባቸው።

وَيَرَى ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلْعِلْمَ ٱلَّذِىٓ أُنزِلَ إِلَيْكَ مِن رَّبِّكَ هُوَ ٱلْحَقَّ
وَيَهْدِىٓ إِلَىٰ صِرَٰطِ ٱلْعَزِيزِ ٱلْحَمِيدِ ٦

6. እነዚያም እውቀትን የተሰጡት ያንን ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን እርሱ እውነትና አሸናፊ ምስጉን ወደ ሆነው አላህ መንገድ የሚመራ መሆኑን ያውቃሉ።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ هَلْ نَدُلُّكُمْ عَلَىٰ رَجُلٍ يُنَبِّئُكُمْ إِذَا مُزِّقْتُمْ كُلَّ مُمَزَّقٍ إِنَّكُمْ لَفِى
خَلْقٍ جَدِيدٍ ٧

7. እነዚያም በአላህ የካዱት (ሙታችሁ) ሙሉ መበጣጠስን በተበጣጠሳችሁ ጊዜ በአዳዲስ መፈጠር ውስጥ ትሆናላችሁ ብሎ የሚነግራችሁን ሰው እናሳያችሁን? አሉ።

**ከሰበእ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-7) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህን ማመስገን እንደሚገባ፤
2. እውቀት ሁሉን ነገር የሚያጠቃልል መሆኑን፤
3. የቂያማ ቀን የማይቀር መሆኑን፤
4. የቁርአን ተዐምርነት በመልዕከቱ ብቻ ሳይሆን በቃልም መሆኑ፤

أَفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًا أَم بِهِۦ جِنَّةٌۢ بَلِ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِٱلْءَاخِرَةِ فِى ٱلْعَذَابِ وَٱلضَّلَٰلِ ٱلْبَعِيدِ ٨

8. በአላህ ላይ ውሸትን ቀጠፈን? ወይስ በእርሱ እብደት አለበት? አሉ። እንዳሉት አይደለም እነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት በእርሷ በቅጣት ውስጥ የሚሆኑና አሁንም በራቀ ስህተት ውስጥ ናቸው።

أَفَلَمۡ يَرَوۡاْ إِلَىٰ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيهِمۡ وَمَا خَلۡفَهُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِۚ إِن نَّشَأۡ نَخۡسِفۡ بِهِمُ
ٱلۡأَرۡضَ أَوۡ نُسۡقِطۡ عَلَيۡهِمۡ كِسَفٗا مِّنَ ٱلسَّمَآءِۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَةٗ لِّكُلِّ عَبۡدٖ مُّنِيبٖ ﴿٩﴾

**9.** ከሰማይና ከምድር በፊታቸውና በኋላቸው ወደ አለው ሁሉ አይመለከቱምን? ብንሻ እኮ በእነርሱ ምድርን እንደረምስባቸዋለን፡፡ ወይም በእነርሱ ላይ ከሰማይ ቁራጭን እንጥልባቸዋለን፡፡ በዚህ ውስጥ ወደ ጌታው ተመላሽ ለሆነ ባሪያ ሁሉ ታላቅ ምልክት አለበት፡፡

۞وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا دَاوُۥدَ مِنَّا فَضۡلٗاۖ يَٰجِبَالُ أَوِّبِي مَعَهُۥ وَٱلطَّيۡرَۖ وَأَلَنَّا لَهُ ٱلۡحَدِيدَ ﴿١٠﴾
أَنِ ٱعۡمَلۡ سَٰبِغَٰتٖ وَقَدِّرۡ فِي ٱلسَّرۡدِۖ وَٱعۡمَلُواْ صَٰلِحًاۖ إِنِّي بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ﴿١١﴾

**10-11.** ለዳውድ ከእኛ የሆነን ችሮታ በእርግጥ ሰጠነው፡፡ (አልንም) ተራራዎች ሆይ፣ ከእሱ ጋር ውዳሴን መላልሱ፡፡ በራሪዎችንም (ገራንለት) ብረትንም ለእሱ አለዘብንለት፡፡ ሰፋፊዎችን ጥሩሮዎች ስራ፡፡ በአሰራርዋም መጥን፡፡ መልካምንም ስራ ስሩ፡፡ እኔ የምትሰሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነኝና (አልነው)፡፡

وَلِسُلَيۡمَٰنَ ٱلرِّيحَ غُدُوُّهَا شَهۡرٞ وَرَوَاحُهَا شَهۡرٞۖ وَأَسَلۡنَا لَهُۥ عَيۡنَ ٱلۡقِطۡرِۖ وَمِنَ ٱلۡجِنِّ مَن
يَعۡمَلُ بَيۡنَ يَدَيۡهِ بِإِذۡنِ رَبِّهِۦۖ وَمَن يَزِغۡ مِنۡهُمۡ عَنۡ أَمۡرِنَا نُذِقۡهُ مِنۡ عَذَابِ ٱلسَّعِيرِ ﴿١٢﴾
يَعۡمَلُونَ لَهُۥ مَا يَشَآءُ مِن مَّحَٰرِيبَ وَتَمَٰثِيلَ وَجِفَانٖ كَٱلۡجَوَابِ وَقُدُورٖ رَّاسِيَٰتٍۚ ٱعۡمَلُوٓاْ
ءَالَ دَاوُۥدَ شُكۡرٗاۚ وَقَلِيلٞ مِّنۡ عِبَادِيَ ٱلشَّكُورُ ﴿١٣﴾

**12-13.** ለሱለይማንም ንፋስን የቀትር በፊት ጉዞዋ የወር መንገድ፤ የቀትር በኋላ ጉዞዋም የወር መንገድ ሲሆን ገራንለት፡፡ የነሀስንም ምንጭ ለእርሱ አፈሰስንለት፡፡ ከአጋንንቶችም በጌታው ፈቃድ በፊቱ የሚሰሩትን (አደረግንለት)፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ከትእዛዛችን ዝንፍ የሚል ካለ ከነዳጅ እሳት ቅጣት እናቀምሰዋለን፡፡ ከምኩራቦች፤ ከምስሎችም እንደ ገንዳ ከሆነ ገበታዎችም፤ ከተደላደለ ታላቅ ድስቶችም የሚሻውን ሁሉ ይሰሩለታል (አልናቸውም) የዳውድ ቤተሰቦች ሆይ፣ አመስጋኞች ሆናችሁ ለጌታችሁ ስሩ፡፡ ከባሮቼ ውስጥ አመስጋኞቹ ጥቂቶች ናቸው፡፡

فَلَمَّا قَضَيْنَا عَلَيْهِ ٱلْمَوْتَ مَا دَلَّهُمْ عَلَىٰ مَوْتِهِۦٓ إِلَّا دَآبَّةُ ٱلْأَرْضِ تَأْكُلُ مِنسَأَتَهُۥ ۖ
فَلَمَّا خَرَّ تَبَيَّنَتِ ٱلْجِنُّ أَن لَّوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ٱلْغَيْبَ مَا لَبِثُوا۟ فِى ٱلْعَذَابِ ٱلْمُهِينِ ﴿١٤﴾

**14.** በእርሱም ላይ ሞትን በፈፀምንበት ጊዜ መሞቱን ብትሩን የምትበላ ተንቀሳቃሽ ምስጥ እንጂ ሌላ አላመለከታቸውም። በወደቀ ጊዜም አጋንንቶች ሩቅን ሚስጥር የሚያውቁ በሆነ ኖሮ በአዋራጅ ስቃይ ውስጥ የማይቆዩ እንደነበሩ ተረዱ።

**ከሰበእ ምዕራፍ ከአንቀፅ (8-14) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. *የአላህ ችሎታ ገደብ የሌለው ፀጋው ተቆጥሮ የማያልቅ መሆኑን፤*
2. *ዓለም ለአላህ ታዛዥና ጠዋት ማታ እሱን የሚያመሰግን የሚያወድስ መሆኑን ይህን መሆኑን የማናውቅ መሆናችንን፤*
3. *የስራን አስፈላጊነት እና ዋጋውን፤*
4. *ሰዎች ምርታቸውን ውጤታማ ለማድረግ በሌሎች መረዳታቸው ችግር እንደሌለው፤*
5. *የነብይነት ስልጣን ከንግስና ስልጣን የሚበልጥ መሆኑንና አላህ ለነብዩላህ ሱለይማን ሁለቱንም እንደሰጣቸው፤*
6. *አላህ ለባሮቹ በተለይ ለነብያቶች የዋለላቸው ውለታ ከባድ መሆኑን፤*
7. *ጅኖች (ገይብን) ከኛ የተሰወረን እንደማያውቁ እንማራለን፤*

لَقَدْ كَانَ لِسَبَإٍ فِى مَسْكَنِهِمْ ءَايَةٌ ۖ جَنَّتَانِ عَن يَمِينٍ وَشِمَالٍ ۖ كُلُوا۟ مِن رِّزْقِ رَبِّكُمْ
وَٱشْكُرُوا۟ لَهُۥ ۚ بَلْدَةٌ طَيِّبَةٌ وَرَبٌّ غَفُورٌ ﴿١٥﴾ فَأَعْرَضُوا۟ فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ سَيْلَ ٱلْعَرِمِ
وَبَدَّلْنَٰهُم بِجَنَّتَيْهِمْ جَنَّتَيْنِ ذَوَاتَىْ أُكُلٍ خَمْطٍ وَأَثْلٍ وَشَىْءٍ مِّن سِدْرٍ قَلِيلٍ ﴿١٦﴾ ذَٰلِكَ
جَزَيْنَٰهُم بِمَا كَفَرُوا۟ ۖ وَهَلْ نُجَٰزِىٓ إِلَّا ٱلْكَفُورَ ﴿١٧﴾

**15-17.** ለሰበእ በመኖሪያቸው በእውነት አስደናቂ ምልክት ነበራቸው። ከግራ ከቀኝ ሁለት አትክልቶች ነበሯቸው። ከጌታችሁ ሲሳይ ብሉ ለእሱም አመስግኑ። አገራችሁ ውብ አገር ናት። ጌታችሁም መሃሪ ነው ተባሉ። አላህን ከማመስገን ዞሩም። በእነርሱም ላይ የግድቡን ጎርፍ ለቀቅንባቸው። በሁለቱ አትክልቶቻቸውም ሌሎች ሁለትን አትክልቶች ባለ መርጋጋ ፍሬዎችን ባለ ጠደቻና ከቁርቁራም ባለ ጥቂት ዛፎችን ለወጥናቸው። በመካዳቸው ምክንያት ይህንን መነዳናቸው። (እንደዚህ ያለውን ቅጣት) በጣም ከሓዲ ለሆነ ሰው ብቻ እንጂ ለሌላው እንሰጣለን?

وَجَعَلۡنَا بَيۡنَهُمۡ وَبَيۡنَ ٱلۡقُرَى ٱلَّتِي بَٰرَكۡنَا فِيهَا قُرٗى ظَٰهِرَةٗ وَقَدَّرۡنَا فِيهَا ٱلسَّيۡرَۖ سِيرُواْ
فِيهَا لَيَالِيَ وَأَيَّامًا ءَامِنِينَ ١٨ فَقَالُواْ رَبَّنَا بَٰعِدۡ بَيۡنَ أَسۡفَارِنَا وَظَلَمُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ فَجَعَلۡنَٰهُمۡ
أَحَادِيثَ وَمَزَّقۡنَٰهُمۡ كُلَّ مُمَزَّقٍۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّكُلِّ صَبَّارٖ شَكُورٖ ١٩

**18-19.** በእነርሱና በዚያች በውስጧ በረከትን ባደረግንባት አገር (በሻም) መካከልም ተከታታይ መንደሮችን አደረግን፡፡ በእርሷም ጉዞን ወሰንን በሌሊቶችም ሆነ በቀኖች ዉስጥ ፀጥተኞች ሆናችሁ ተጓዙ (አልን)፡፡ ጌታችን ሆይ፣ በጉዞዎቻችን መካከል አራርቅልን አሉም፡፡ ነፍሶቻቸውንም በደሉ፡፡ መገረሚያ ወሬዎችም አደረግናቸው፡፡ መበታተንንም ሁሉ በታተንናቸው፡፡ በዚህ ውስጥ በጣም ታጋሽና አመስጋኝ ለሆነ ሁሉ ብዙ መገለጫዎች አሉበት፡፡

وَلَقَدۡ صَدَّقَ عَلَيۡهِمۡ إِبۡلِيسُ ظَنَّهُۥ فَٱتَّبَعُوهُ إِلَّا فَرِيقٗا مِّنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٢٠ وَمَا كَانَ لَهُۥ
عَلَيۡهِم مِّن سُلۡطَٰنٍ إِلَّا لِنَعۡلَمَ مَن يُؤۡمِنُ بِٱلۡأٓخِرَةِ مِمَّنۡ هُوَ مِنۡهَا فِي شَكّٖۗ وَرَبُّكَ عَلَىٰ كُلِّ
شَيۡءٍ حَفِيظٞ ٢١ قُلِ ٱدۡعُواْ ٱلَّذِينَ زَعَمۡتُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ لَا يَمۡلِكُونَ مِثۡقَالَ ذَرَّةٖ فِي
ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَلَا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَا لَهُمۡ فِيهِمَا مِن شِرۡكٖ وَمَا لَهُۥ مِنۡهُم مِّن ظَهِيرٖ ٢٢ وَلَا تَنفَعُ
ٱلشَّفَٰعَةُ عِندَهُۥٓ إِلَّا لِمَنۡ أَذِنَ لَهُۥۚ حَتَّىٰٓ إِذَا فُزِّعَ عَن قُلُوبِهِمۡ قَالُواْ مَاذَا قَالَ رَبُّكُمۡۖ قَالُواْ
ٱلۡحَقَّۖ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡكَبِيرُ ٢٣

**20-23.** ኢብሊስም በእነርሱ ላይ ምኞቱን በእርግጥ ፈፀመ፡፡ እናም ከአመኑት የሆኑት ጭፍሮች በስተቀር ተከተሉት፡፡ በመጨረሻይቱም ዓለም የሚያምነውን ከዚያ እርሱ ከእርሷ በመጠራጠር ውስጥ ከሆነው ሰው ለይተን እንድናውቅ እንጂ በእነርሱ ላይ ለእርሱ ምንም ስልጣን አልነበረውም፡፡ ጌታህም በነገሩ ሁሉ ላይ ተጠባባቂ ነው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ከአላህ ሌላ አማልክት ብላችሁ የምታስቧቸውን ጥሩ፡፡ በሰማያትም ሆነ በምድር ውስጥ የብናኝ ክብደት ያህል ምንም አይችሉም፡፡ ለእነርሱም በሁለቱም ውስጥ ምንም ሽርክና የላቸውም፡፡ ከእነርሱም ለእርሱ ምንም አጋዥ የለውም በላቸው፡፡ ምልጃም እርሱ ለፈቀደለት ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ እሱ ዘንድ ምንም አትጠቅምም፡፡ ከልቦቻቸው ላይ ድንጋጤው በተገለጠ ጊዜ ተማላጆቹ ጌታችሁ ምን አለ? ይላሉ፡፡ አማላጆች እውነትን አለ እርሱም ከፍተኛውና ታላቁ ጌታ ነው ይላሉ፡፡

**ከሰበእ ምዕራፍ ከአንቀፅ (15-22) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን ፀጋ መካድና አላህን አለማመስገን የግፍ ሁሉ ግፍ መሆኑን፤
2. በነብያቶች ታሪክ ውስጥ አስተማሪና ጠቃሚ ምክሮች መኖራቸውን፤
3. ቁርኣን ነብዩ (ﷺ) ያውቁት ያልነበረውን ታሪክ በማውሳት ከአላህ መሆኑን ማረጋገጡን፤
4. ንግድና ሌሎች የዕለት ጉርስ ለመግኘትና ራስን ለመቻል የሚደረጉ ሩጫዎች አላህ ከሚወዳቸው ጉዳዮች እንደሆኑ፤
5. ሰይጣንን መከተል እንደሌለብንና ጥሪውን መቀበል እንደሌለብን፤

۞قُلْ مَن يَرْزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ قُلِ ٱللَّهُ ۖ وَإِنَّآ أَوْ إِيَّاكُمْ لَعَلَىٰ هُدًى أَوْ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٢٤﴾ قُل لَّا تُسْـَٔلُونَ عَمَّآ أَجْرَمْنَا وَلَا نُسْـَٔلُ عَمَّا تَعْمَلُونَ ﴿٢٥﴾ قُلْ يَجْمَعُ بَيْنَنَا رَبُّنَا ثُمَّ يَفْتَحُ بَيْنَنَا بِٱلْحَقِّ وَهُوَ ٱلْفَتَّاحُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٢٦﴾

**24-26.** (ሙሐመድ ሆይ)፣ ከሰማያትና ከምድር ዝናብንና ቡቃያን የሚሰጣችሁ ማነው? በላቸው፡፡ አላህ ነው እኛ ወይም እናንተ በትክክለኛው መንገድ ላይ ወይም በግልፅ መሳሳት ውስጥ ነን በላቸው፡፡ ሙሐመድ ሆይ፣ ከአጠፋነው ጥፋት አትጠየቁም፡፡ ከምትሰሩትም ስራ አንጠየቅም በላቸው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታችን በመካከላችን ይሰበስባል ከዚያ በመካከላችን በእውነት ይፈርዳል እርሱም በትክክል ፈራጅና አዋቂ ነው በላቸው፡፡

قُلْ أَرُونِىَ ٱلَّذِينَ أَلْحَقْتُم بِهِۦ شُرَكَآءَ ۖ كَلَّا ۚ بَلْ هُوَ ٱللَّهُ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ﴿٢٧﴾

**27.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ተጋሪዎች አድርጋችሁ በእሱ ያስጠጋችኋቸውን ጣዖታት እስቲ አሳዩኝ፡፡ (ሙሐመድ ሆይ)፣ ተው አታጋሩ በእውነት እርሱ አሸናፊና ብልሃተኛ አላህ ነው በላቸው፡፡

وَمَآ أَرْسَلْنَٰكَ إِلَّا كَآفَّةً لِّلنَّاسِ بَشِيرًا وَنَذِيرًا وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٢٨﴾

**28.** አንተንም ለሰዎች ሁሉ በመላ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን ቢሆን እንጂ አልላክንህም፡፡ ግን አብዛኞቹ ሰዎች አያውቁም፡፡

وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلْوَعْدُ إِن كُنتُمْ صَٰدِقِينَ ﴿٢٩﴾ قُل لَّكُم مِّيعَادُ يَوْمٍ لَّا تَسْتَـْٔخِرُونَ عَنْهُ سَاعَةً وَلَا تَسْتَقْدِمُونَ ﴿٣٠﴾

**29-30.** እውነተኞችም እንደ ሆናችሁ ይህ ቀጠሮ መቼ ነው? ይላሉ፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእናንተ ከእርሱ አንዳችንም ሰዓት የማትዘገዩበት የማትቀድሙበትም የቀጠሮ ቀን አላችሁ በላቸው፡፡

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَن نُّؤْمِنَ بِهَٰذَا ٱلْقُرْءَانِ وَلَا بِٱلَّذِى بَيْنَ يَدَيْهِ ۗ وَلَوْ تَرَىٰٓ إِذِ ٱلظَّٰلِمُونَ
مَوْقُوفُونَ عِندَ رَبِّهِمْ يَرْجِعُ بَعْضُهُمْ إِلَىٰ بَعْضٍ ٱلْقَوْلَ يَقُولُ ٱلَّذِينَ ٱسْتُضْعِفُوا۟ لِلَّذِينَ
ٱسْتَكْبَرُوا۟ لَوْلَآ أَنتُمْ لَكُنَّا مُؤْمِنِينَ ﴿٣١﴾

31. እነዚያ የካዱትም በዚህ ቁርአንና በዚያ ከበፊቱ ባለውም መጽሐፍ በጭራሽ አናምንም አሉ፡፡ በዳዮችም ከፊላቸው ወደ ከፊሉ ንግግርን የሚመላለሱ ሆነው በጌታቸው ዘንድ በሚቆሙ ጊዜ ብታይ ኖሮ (አስደናቂን ነገር ታይ ነበር)፡፡ እነዚያ የተዋረዱት ለእነዚያ ለኮሩት እናንተ ባልነበራችሁ ኖሮ አማኞች በሆንን ነበር ይላሉ፡፡

**ከሰበእ ምዕራፍ ከአንቀፅ (23-31) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የምንዳ መሰረቱ እምነትና መልካም ስራ እንጂ ገንዘብ አለመሆኑ፤
2. ቁርአን የሰውን ልጅ አዕምሮ የሚያከብርና ውጤታማ ውይይትን የሚያበረታታ መሆኑን፤
3. አላህ መልዕክተኛውን የሚያበረታታና ልባቸውን የሚያፅናና መሆኑን፤
4. ነብዩ (ﷺ) ለሰው ልጅ በጠቅላላ የተላኩና የነብያት መደምደሚያ መሆናቸውን፤
5. ሸፈዓ በአላህ ፈቃድ ብቻ የሚሆን ሸፈዓን ደግሞ ከአማኞቹ ሌላ ለማንም የማይፈቀድ መሆኑን፤

قَالَ ٱلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُوا۟ لِلَّذِينَ ٱسْتُضْعِفُوٓا۟ أَنَحْنُ صَدَدْنَٰكُمْ عَنِ ٱلْهُدَىٰ
بَعْدَ إِذْ جَآءَكُم ۖ بَلْ كُنتُم مُّجْرِمِينَ ﴿٣٢﴾

32. እነዚያ የኮሩት ለእነዚያ ለተዋረዱት ትክክለኛው እምነት ከመጣላችሁ በኋላ እኛ ከለከልናችሁን? አይደለም እናንተው ከሓዲያን ነበራችሁ ይሏቸዋል፡፡

وَقَالَ ٱلَّذِينَ ٱسْتُضْعِفُوا۟ لِلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُوا۟ بَلْ مَكْرُ ٱلَّيْلِ وَٱلنَّهَارِ إِذْ تَأْمُرُونَنَآ أَن نَّكْفُرَ
بِٱللَّهِ وَنَجْعَلَ لَهُۥٓ أَندَادًا ۚ وَأَسَرُّوا۟ ٱلنَّدَامَةَ لَمَّا رَأَوُا۟ ٱلْعَذَابَ ۚ وَجَعَلْنَا ٱلْأَغْلَٰلَ فِىٓ أَعْنَاقِ
ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ۚ هَلْ يُجْزَوْنَ إِلَّا مَا كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿٣٣﴾

33. እነዚያም የተዋረዱት ለእነዚያ ለኮሩት አይደለም በአላህ እንድንክድና ለእርሱ ባላንጣዎችን እንድናደርግ ስታዙን የከለከለን የሌሊትና የቀን ዱለታችሁ ነው ይላሉ፡፡ ቅጣትንም ባዩ ጊዜ ፀፀትን ይገልጻሉ (ይደብቃሉ)፡፡ በእነዚያ በካዱት አንገቶች ላይ እንዛዝሎችን እናደርጋለን፡፡ ይሰሩት የነበሩትን እንጂ ሌላን ይመነዳሉን?

وَمَآ أَرْسَلْنَا فِى قَرْيَةٍ مِّن نَّذِيرٍ إِلَّا قَالَ مُتْرَفُوهَآ إِنَّا بِمَآ أُرْسِلْتُم بِهِۦ كَٰفِرُونَ ٣٤
وَقَالُوا۟ نَحْنُ أَكْثَرُ أَمْوَٰلًا وَأَوْلَٰدًا وَمَا نَحْنُ بِمُعَذَّبِينَ ٣٥

**34-35.** በየትኛዋም ከተማ አስፈራሪን አላክንም ተቀማጣዩችዋ እኛ በተላካችሁት ከሓዲዎች ነን ያሉ ቢሆኑ እንጂ። እኛ በገንዘቦችና በልጆች ይበልጥ የበዛን ነን። እኛም የምንቀጣ አይደለንም አሉ።

*ከሰበእ ምዕራፍ (34) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሁለት ጓደኛሞች በመካ ይኖሩ ነበር። አንደኛው ለንግድ ወደ ሻም እንደሄደ ሙሐመድ ስለተላኩና ወሬው ስለተናፈሰ «ለጓደኛው ምን ተፈጠረ» ብሎ መልዕክት ላከበት። ጓደኛውም «ድሆችና አነስተኛ ኑሮ ያላቸው ናቸው የተከተሉት» ብሎ መልስ ጻፈለት። በዚህ ጊዜ ንግዱን ትቶ ወደ መካ በመምጣት «የት አለ ይህ ሰውዬ አሳየኝ» በማለት ጓደኛውን ጠይቆ ወደ ነብዩ ሲያደርሰው «ሙሐመድ ሆይ! ወደ ምንድን ነው ጥሪ የምታደርገው» ብሎ ጠየቃቸው። ነብዩም የሚያስተምሩትን ነገር አንድ በአንድ ሲዘረዝሩለት «የአላህ መልክተኛ ለመሆንህ እመስክራሁ» አላቸው። ነብዩም (ﷺ) «በምን አወክ የአላህ መልዕክተኛ መሆኔን» አሉት። መፅሐፎችን ያነብ ስለነበር «ማንም ነብይ መጀመሪያ ሲላክ የሚከተሉት ችግረኞች እና ደካሞች ናቸውና» አላቸው በዚህ ጊዜ ይህ የቁርኣን አንቀፅ ወረደ። (ሱዩጢ)*

قُلْ إِنَّ رَبِّى يَبْسُطُ ٱلرِّزْقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقْدِرُ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعْلَمُونَ ٣٦
وَمَآ أَمْوَٰلُكُمْ وَلَآ أَوْلَٰدُكُم بِٱلَّتِى تُقَرِّبُكُمْ عِندَنَا زُلْفَىٰٓ إِلَّا مَنْ ءَامَنَ وَعَمِلَ صَٰلِحًا
فَأُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ جَزَآءُ ٱلضِّعْفِ بِمَا عَمِلُوا۟ وَهُمْ فِى ٱلْغُرُفَٰتِ ءَامِنُونَ ٣٧ وَٱلَّذِينَ يَسْعَوْنَ فِىٓ
ءَايَٰتِنَا مُعَٰجِزِينَ أُو۟لَٰٓئِكَ فِى ٱلْعَذَابِ مُحْضَرُونَ ٣٨

**36-38.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ ሲሳይን ለሚሻው ሰው ሁሉ ያሰፋል። ለሚሻው ሰውም ሁሉ ያጠባል። ግን አብዛኛዎች ሰዎች ይህን አያውቁም በላቸው። ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁም ያች እኛ ዘንድ መቅረብን የምታቀርባችሁ አይደለችም። ያ! በትክክል ያመነና መልካምን የሰራ ብቻ ሲቀር። እነዚያ ለእነርሱ በሰሩት መልካም ስራ እጥፍ ምንዳ አለላቸው። እነርሱም በገነት ሰገነቶች ውስጥ ፀጥተኞች ናቸው። እነዚያ የሚያቅቱ መስሏቸው አንቀፆቻችንን ለማበላሸት የሚጥሩ ሁሉ እነዚያ በቅጣት ውስጥ የሚጣዱ ናቸው።

قُلْ إِنَّ رَبِّى يَبْسُطُ ٱلرِّزْقَ لِمَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ وَيَقْدِرُ لَهُۥ ۚ وَمَآ أَنفَقْتُم مِّن شَىْءٍ فَهُوَ
يُخْلِفُهُۥ ۖ وَهُوَ خَيْرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ٣٩

**39.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ ሲሳይን ከባሮቹ ለሚሻው ሰው ያሰፋል። ለእርሱም ያጠባል። ከማንኛውም ነገር የምትለግሱትን እርሱ ይተካዋል። እርሱም ከሲሳይ ሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነው በላቸው።

**ከሰበእ ምዕራፍ ከአንቀፅ (32-39) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ጣኦት አምላኪዎች አምላክ አድርገው የያዟቸው አማልክት ለተከታዩች ምንም እንደማይጠቅሙ፤
2. አላህ አይቀጣንም እያሉ የሚከራከሩ ከሓዲያን መረጃ የሌለው ክርክር መሆኑን፤
3. ሪዝቅ በአንድ አላህ እጅ ብቻ መሆኑን፤
4. የሪዝቅ መስፋትም ሆነ መጥበብ የአላህ መውደድ ወይም የመጥላት ምልክት እንዳልሆነ፤
5. ለአላህ ብሎ መስጠት ከፍተኛ ምንዳ እንዳለው እንማራለን።

وَيَوۡمَ يَحۡشُرُهُمۡ جَمِيعٗا ثُمَّ يَقُولُ لِلۡمَلَٰٓئِكَةِ أَهَٰٓؤُلَآءِ إِيَّاكُمۡ كَانُواْ يَعۡبُدُونَ ٤٠ قَالُواْ
سُبۡحَٰنَكَ أَنتَ وَلِيُّنَا مِن دُونِهِمۖ بَلۡ كَانُواْ يَعۡبُدُونَ ٱلۡجِنَّۖ أَكۡثَرُهُم بِهِم مُّؤۡمِنُونَ ٤١
فَٱلۡيَوۡمَ لَا يَمۡلِكُ بَعۡضُكُمۡ لِبَعۡضٖ نَّفۡعٗا وَلَا ضَرّٗا وَنَقُولُ لِلَّذِينَ ظَلَمُواْ ذُوقُواْ عَذَابَ ٱلنَّارِ
ٱلَّتِي كُنتُم بِهَا تُكَذِّبُونَ ٤٢

**40-42.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሁሉንም በሚሰበስባቸውና ከዚያም ለመላእክቶቹ እነዚህ እናንተን ይገዙ ነበሩን በሚላቸው ቀን (የሚሆነውን አስታውስ)። መላእክቶችም ጥራት ይገባህ ከእነርሱ ሌላ ረዳታችን አንተ ብቻ ነህ። እንደሚሉት አይደለም። ይልቁንም አጋንንትን ይገዙ ነበሩ። አብዛኞቻቸው በእነርሱ አማኞች ናቸው ይላሉ። ዛሬ ከፊላችሁ ለከፊሉ መጥቀምንም ሆነ መጉዳትን አይችሉም። ለእነዚያም ለበደሉት ያችን በእርሷ ታስተባብሉባት የነበራችሁትን የእሳት ቅጣት ቅመሱ እንላቸዋለን።

وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُنَا بَيِّنَٰتٖ قَالُواْ مَا هَٰذَآ إِلَّا رَجُلٞ يُرِيدُ أَن يَصُدَّكُمۡ عَمَّا كَانَ يَعۡبُدُ
ءَابَآؤُكُمۡ وَقَالُواْ مَا هَٰذَآ إِلَّآ إِفۡكٞ مُّفۡتَرٗىۚ وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِلۡحَقِّ لَمَّا جَآءَهُمۡ إِنۡ هَٰذَآ
إِلَّا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ٤٣

**43.** በእርሱም ላይ አንቀፆቻችን ግልፅ ሆነው በተነበቡላቸው ጊዜ ይህ አባቶቻችሁ ይገዙት ከነበሩት ነገር ሊከለክላችሁ የሚፈልግ ሰው እንጂ ሌላ አይደለም አሉ። ይህም ቁርዓን የተቀጣጠፈ ውሸት ነው እንጂ ሌላ አይደለም አሉ። እነዚያ በአላህ የካዱት እውነትን በመጣላቸው ጊዜ ይህ ግልጽ ድግምት ነው እንጂ ሌላ አይደለም አሉ።

وَمَآ ءَاتَيۡنَٰهُم مِّن كُتُبٖ يَدۡرُسُونَهَاۖ وَمَآ أَرۡسَلۡنَآ إِلَيۡهِمۡ قَبۡلَكَ مِن نَّذِيرٖ ﴿٤٤﴾ وَكَذَّبَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ وَمَا بَلَغُواْ مِعۡشَارَ مَآ ءَاتَيۡنَٰهُمۡ فَكَذَّبُواْ رُسُلِيۖ فَكَيۡفَ كَانَ نَكِيرِ ﴿٤٥﴾

**44-45.** የሚያጠኗቸው የሆኑ መጽሐፎችንም ምንም አልሰጠናቸውም፡፡ ከአንተ በፊትም አስፈራሪ ነብይን ወደ እነርሱ አልላክንም፡፡ እነዚያም ከእነርሱ በፊት የነበሩት አስተባብለዋል፡፡ የሰጠናቸውንም ከአስር አንዱን እነዚህ አልደረሱም መልዕክተኞቼንም አስተባበሉ፡፡ ነቀፍኳቸውም፡፡ መንቀፌም እንዴት ነበር፡፡

۞ قُلۡ إِنَّمَآ أَعِظُكُم بِوَٰحِدَةٍۖ أَن تَقُومُواْ لِلَّهِ مَثۡنَىٰ وَفُرَٰدَىٰ ثُمَّ تَتَفَكَّرُواْۚ مَا بِصَاحِبِكُم مِّن جِنَّةٍۚ إِنۡ هُوَ إِلَّا نَذِيرٞ لَّكُم بَيۡنَ يَدَيۡ عَذَابٖ شَدِيدٖ ﴿٤٦﴾

**46.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የምንገስጻችሁ በአንዲት ነገር ብቻ ነው እርሷም ሁለት ሁለት አንድ አንድም ሆናችሁ ለአላህ እንድትነሱና ከዚያ በጓደኛችሁ (በሙሐመድ) ምንም እብደት የሌለበት መሆኑን መርምራችሁ እንድትረዱ ነው፡፡ እርሱ ለእናንተ ከብርቱ ቅጣት በስተፊት አስጠንቃቂ ነው እንጂ ሌላ አይደለም በላቸው፡፡

قُلۡ مَا سَأَلۡتُكُم مِّنۡ أَجۡرٖ فَهُوَ لَكُمۡۖ إِنۡ أَجۡرِيَ إِلَّا عَلَى ٱللَّهِۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٞ ﴿٤٧﴾

**47.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዋጋ ማንኛውንም የጠየቅኋችሁ ቢኖር እርሱ ለእናንተው ነው፡፡ ዋጋዬ በአላህ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይደለም፡፡ እርሱም በነገሩ ሁሉ አዋቂ ነው በላቸው፡፡

قُلۡ إِنَّ رَبِّي يَقۡذِفُ بِٱلۡحَقِّ عَلَّٰمُ ٱلۡغُيُوبِ ﴿٤٨﴾

**48.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታዬ፣ እውነትን ያወርዳሉ፡፡ ሩቅ የሆኑትን ምስጢሮች ሁሉ አዋቂ ነው በላቸው፡፡

قُلۡ جَآءَ ٱلۡحَقُّ وَمَا يُبۡدِئُ ٱلۡبَٰطِلُ وَمَا يُعِيدُ ﴿٤٩﴾ قُلۡ إِن ضَلَلۡتُ فَإِنَّمَآ أَضِلُّ عَلَىٰ نَفۡسِيۖ وَإِنِ ٱهۡتَدَيۡتُ فَبِمَا يُوحِيٓ إِلَيَّ رَبِّيٓۚ إِنَّهُۥ سَمِيعٞ قَرِيبٞ ﴿٥٠﴾

**49-50.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እውነቱ መጣ ውሸት መነሻም መድረሻም የለውምና (ተወገደ) በላቸው፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ብሳሳት የምሳሳተው በራሴ ላይ ብቻ ነው፡፡ ብመራም ጌታዬ ወደ እኔ በሚያወርደው መመሪያ መሰረት ነው፡፡ እርሱ ሰሚ ቅርብ ነውና በላቸው፡፡

وَلَوْ تَرَىٰٓ إِذْ فَزِعُوا۟ فَلَا فَوْتَ وَأُخِذُوا۟ مِن مَّكَانٍ قَرِيبٍ ﴿٥١﴾ وَقَالُوٓا۟ ءَامَنَّا بِهِۦ وَأَنَّىٰ لَهُمُ ٱلتَّنَاوُشُ
مِن مَّكَانٍۭ بَعِيدٍ ﴿٥٢﴾ وَقَدْ كَفَرُوا۟ بِهِۦ مِن قَبْلُ ۖ وَيَقْذِفُونَ بِٱلْغَيْبِ مِن مَّكَانٍۭ بَعِيدٍ ﴿٥٣﴾ وَحِيلَ
بَيْنَهُمْ وَبَيْنَ مَا يَشْتَهُونَ كَمَا فُعِلَ بِأَشْيَاعِهِم مِّن قَبْلُ ۚ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ فِى شَكٍّ مُّرِيبٍۭ ﴿٥٤﴾

**51-54.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በደነገጡና ማምለጫ በሌላቸው ጊዜ ከቅርብ ስፍራም በተያዙ ጊዜ ሁኔታቸውን ብታይ ኖሮ (አስደናቂን ነገር ባየህ ነበር)። በእርሱም አሁን እመን ይላሉ። ለእነርሱም ከሩቅ ስፍራ እምነትን በቀላል ማግኘት ከየታቸው ይታደላሉ? በፊትም በእርሱ በእርግጥ ክደዋል። ከሩቅ ስፍራም በግምት ንግግርን ይጥላሉ። ከዚህ ቀደም በመሰሎቻቸው እንደተሰራውም ብጤ በእነርሱና በሚፈልጉት መካከል ተጋረደ። እነርሱ በእርግጥ በአወላዋይ ጥርጣሬ ውስጥ ነበሩና።

**ከሰበእ ምዕራፍ ከአንቀፅ (40-54) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. *መላእክት ራሳቸው የአላህ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን፤*
2. *መላእክት ራሳቸው የአላህን ውዴታ ለማግኘት ጠዋት ማታ በአምልኮት ላይ ያሉ መሆናቸውን፤*
3. *መላእክት ራሳቸው ሊመለኩ የማይገባቸው መሆኑን፤*
4. *ወደ አላህ በጥበብና በመልካም ምክር ማስተማር ግዴታ መሆኑን እንማራለን።*

በአላህ ፈቃድ የሰበእ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (35)
# የፈጣሪ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ፋጢር)

سُورَةُ فَاطِرٍ

## በመካ ነው የወረደው። የአናቅፅ ብዛት (45) ናቸው።
## የሱረቱ ፋጢር መግቢያ

ይህ ምዕራፍ የመላኢካ ምዕራፍ በመባልም ይታወቃል። አስተምህሮቱን የሚጀምረው ሰማያትንና ምድርን ያለ ቢጤ ለፈጠረ ጌታ ምስጋናና ሙገሳ የሚገባው መሆኑን መግለፅ ነው።

አላህ ለፍጡሮቹ የሰጠውን ማንም አይከለክልም። የከለከለውንም እንዲሁ ማንም አይሰጥም። ለእነዚህ ሰዎች ቢያስተባብሉህም ከአንተ በፊት ባለፉት ነብያት ታሪክና እምነት መልስ በሰጠንህ ልትፅናና ይገባል ይላል።

ሰዎች በዚህች አለም ደስታና ምቾት ሊሸነገሉና ሰይጣን ሊያሞኛቸው እንደማይገባ ይመክራል። ክብር የፈለገ በአላህ ይከብራል። አላህን የለቀቀ ግን ይዋረዳል። የሰዎች ተግባር በሙሉ ሲቀርብለት የሙዕሚኖችን ተቀብሎ የከሀዲዎችን ይመልሳል። አላህ የሞተን መቀስቀስ እንደሚችል የሚያስረዱ ተዓምራት ሰውን ከአፈር፤ ከዚያ ከጠብታ ፈጥሮ የሁለት ፆታ ባለቤት አድርጎ ፈጥሮታል። አላህ ወንድንና ሴትን የፈጠረ፤ እርጉዝ ሴትም ስታረግዝ ምን እንዳረገዘችና መቼ እንደምትወልድ፤ ልጁም ወደ ፊት ምን ሊሆን እንደሚችል፤ እውቀቱ የእሱ ብቻ መሆኑን ያስተምራል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ فَاطِرِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ جَاعِلِ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةِ رُسُلًا أُوْلِيٓ أَجۡنِحَةٖ مَّثۡنَىٰ وَثُلَٰثَ وَرُبَٰعَۚ يَزِيدُ فِي ٱلۡخَلۡقِ مَا يَشَآءُۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ١

**1.** ምስጋና ሁሉ ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ መላእክትን ባለ ሁለት ሁለት፤ ባለ ሶስት ሶስትና ባለ አራት አራት ክንፎች የሆኑ መልክተኞች አድራጊ ለሆነው አላህ ይገባው። በፍጥረቱ ውስጥ የሚሻውን ይጨምራል። አላህ በሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነውና።

مَّا يَفۡتَحِ ٱللَّهُ لِلنَّاسِ مِن رَّحۡمَةٖ فَلَا مُمۡسِكَ لَهَاۖ وَمَا يُمۡسِكۡ فَلَا مُرۡسِلَ لَهُۥ مِنۢ بَعۡدِهِۦۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٢

**2.** አላህ ለሰዎች ከችሮታ የሚከፍታትን ለእርሷ ምንም አጋጅ የላትም። የሚያግደውም ከእርሱ በኋላ ለእርሱ ምንም ለቃቂ የለውም። እርሱ ብቸኛ፤ አሸናፊ፤ ጥበበኛ ነውና።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ ٱذۡكُرُواْ نِعۡمَتَ ٱللَّهِ عَلَيۡكُمۡۚ هَلۡ مِنۡ خَٰلِقٍ غَيۡرُ ٱللَّهِ يَرۡزُقُكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَٱلۡأَرۡضِۚ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ فَأَنَّىٰ تُؤۡفَكُونَ ٣ وَإِن يُكَذِّبُوكَ فَقَدۡ كُذِّبَتۡ رُسُلٞ مِّن قَبۡلِكَۚ وَإِلَى ٱللَّهِ تُرۡجَعُ ٱلۡأُمُورُ ٤

**3-4.** እናንተ ሰዎች ሆይ! በእናንተ ላይ ያለውን የአላህን ፀጋ አስታውሱ። ከአላህ ሌላ ከሰማይም ሆነ ከምድር ሰጪ ፈጣሪ አለን?። ከእርሱ በስተቀር ትክክለኛ አምላክ የለም። ታዲያ ወዴት ትዞራለችሁ? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢያስተባብሉህም ከአንተ በፊት የነበሩ ነብያትም ህዝቦቻቸው አስተባብለዋቸዋል። የሁሉ ነገር መመለሻ ወደ አላህ ብቻ ነው።

**ከፈጣሪ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-3) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *አላህን ማመስገን ተገቢ ስለመሆኑ፤*
2. *የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤*
3. *ኸይርን ለማግኘትም ሆነ መጥፎን ለመካለካል ወደ አላህ መጠጋት አማራጭ የሌለው ብቸኛ መንገድ ስለመሆኑ፤*
4. *ለማመስገን እንዲያስችል የአላህን ፀጋዎች ማውሳቱ ግዴታ ስለመሆኑ፤*
5. *ተውሒድን በማስረጃ ማረጋገጥ፤*
6. *በከሓዲያን ባህሪ መገረምና መደነቅ እንደማይገባን እንማራለን።*

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّۖ فَلَا تَغُرَّنَّكُمُ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا وَلَا يَغُرَّنَّكُم بِٱللَّهِ
ٱلْغَرُورُ ۝٥ إِنَّ ٱلشَّيْطَـٰنَ لَكُمْ عَدُوٌّ فَٱتَّخِذُوهُ عَدُوًّاۚ إِنَّمَا يَدْعُواْ حِزْبَهُۥ لِيَكُونُواْ مِنْ
أَصْحَـٰبِ ٱلسَّعِيرِ ۝٦

5-6. (እናንተ ሰዎች ሆይ)፣ የአላህ ቀጠሮ እውነት ነው፡፡ እናም የቅርቢቱ ህይወት አታታላችሁ፡፡ አታላዩም ሰይጣን በአላህ ትዕዛዝ ላይ አያታላችሁ፡፡ ሰይጣን ለእናንተ የለየለት ጠላት ነውና፡፡ ስለዚህ እሱን ጠላት አድርጋችሁ ያዙት፡፡ ሰይጣን ተከታዮቹን የሚጠራው ከእሳት ጓዶች እንዲሆኑ ብቻ ነው፡፡

ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ لَهُم مَّغْفِرَةٌ وَأَجْرٌ كَبِيرٌ ۝٧

7. እነዚያ የካዱት ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አለባቸው፡፡ እነዚያም በአላህ ያመኑትና በጎ ስራዎችን የሰሩት ሁሉ ለእነርሱ በአላህ ዘንድ ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው፡፡

أَفَمَن زُيِّنَ لَهُۥ سُوٓءُ عَمَلِهِۦ فَرَءَاهُ حَسَنًاۖ فَإِنَّ ٱللَّهَ يُضِلُّ مَن يَشَآءُ وَيَهْدِى مَن يَشَآءُۖ
فَلَا تَذْهَبْ نَفْسُكَ عَلَيْهِمْ حَسَرَٰتٍۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌۢ بِمَا يَصْنَعُونَ ۝٨

8. መጥፎ ስራው የተሸለመለትና መልካም አድርጎ ያየው ሰው አላህ እንዳቀናው ሰው ነውን? አላህ የሚፈልገውን ሰው ያጠማል፡፡ የሚፈልገውንም ያቀናል፡፡ ስለዚህ እነርሱ ባለ መቅናታቸው በመቆላጨት ነፍስህን አታጥፋ፡፡ አላህ የሚሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነውና፡፡

وَٱللَّهُ ٱلَّذِىٓ أَرْسَلَ ٱلرِّيَـٰحَ فَتُثِيرُ سَحَابًا فَسُقْنَـٰهُ إِلَىٰ بَلَدٍ مَّيِّتٍ فَأَحْيَيْنَا بِهِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ
مَوْتِهَاۚ كَذَٰلِكَ ٱلنُّشُورُ ۝٩

9. አላህ ያ! ንፋሶችን የላከ ነው፡፡ ከዚያ ንፋሶች ዳመናዎችን ትቀሰቅሳለች ወደ ሙት (ድርቅ) አገርም እንነዳዋለን፡፡ በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ህያው እናደርጋታለን ሙታንንም መቀስቀስ ልክ እነደዚሁ ነው፡፡

مَن كَانَ يُرِيدُ ٱلْعِزَّةَ فَلِلَّهِ ٱلْعِزَّةُ جَمِيعًاۚ إِلَيْهِ يَصْعَدُ ٱلْكَلِمُ ٱلطَّيِّبُ وَٱلْعَمَلُ ٱلصَّـٰلِحُ يَرْفَعُهُۥۚ
وَٱلَّذِينَ يَمْكُرُونَ ٱلسَّيِّـَٔاتِ لَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌۖ وَمَكْرُ أُوْلَـٰٓئِكَ هُوَ يَبُورُ ۝١٠

**10.** ማሸነፍን የሚፈልግ ሰው አሸናፊነት ለአላህ ብቻ ነው። (እርሱን በመገዛት ይፈልገው)። መልካም ንግግር ወደ እርሱ ይወጣል። በጎ ስራም ባለቤቱን ከፍ ያደርገዋል። እነዚያ መጥፎ ስራዎችን የሚዶልቱ ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አለባቸው። የእነዚያም ተንኮል እርሱ ይጠፋል።

وَٱللَّهُ خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطۡفَةٍ ثُمَّ جَعَلَكُمۡ أَزۡوَٰجًاۚ وَمَا تَحۡمِلُ مِنۡ أُنثَىٰ
وَلَا تَضَعُ إِلَّا بِعِلۡمِهِۦۚ وَمَا يُعَمَّرُ مِن مُّعَمَّرٖ وَلَا يُنقَصُ مِنۡ عُمُرِهِۦٓ إِلَّا فِي كِتَٰبٍۚ
إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ ١١

**11.** አላህም ከአፈር ከዚያ ከፍትወት ጠብታ ፈጠራችሁ። ከዚያ ጎሳዎች አደረጋችሁ። የትኛዋም ሴት አታረግዝም አትወልድምም በእውቀቱ ቢሆን እንጂ። እድሜው ከሚረዝምለትም አንድም አይረዘምለትም ከእድሜውም አይጎድልበትም በመጽሀፉ ውስጥ ያለ ቢሆን እንጂ። ይህ በአላህ ላይ ገር ነው።

**ከፈጣሪ ምዕራፍ ከአንቀፅ (4-11) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ነብዩን (ﷺ) እና ዳኢዎችን ማፅናናት፤
2. የሙቶ መነሳት ሀቅነት ማረጋገጥ፤
3. በዚህች አለም ምኞትና ድሎት ከመታለል ማስጠንቀቅ፤
4. በሰይጣን ከመሸንገል ማስጠንቀቅና የሰይጣንን ጠላትነት ማሳወቅ፤
5. የሰይጣን ጠላቶችና የአላህ ወዳጆች እንዲሁም የአላህ የጠላቶችና የሰይጣን ወዳጆች ምንዳቸው ምን ምን እንደሚሆን፤
6. የሰይጣንን ስሜት ከመከተል ማስጠንቀቅ፤
7. ምድር ከደረቀችና ከሞተች በኋላ ህያው ማድረግ ከሞት በኋላ መቀስቀስ እንዳለ የሚያረጋግጥ ግልፅ ማስረጃ ስለ መሆኑ፤
8. ክብርን ማግኘት የሚቻለው በአላህ መንገድ በመመራት ብቻ ስለ መሆኑና ትልቅ ነገር መሆኑን እንማራለን።

وَمَا يَسۡتَوِي ٱلۡبَحۡرَانِ هَٰذَا عَذۡبٞ فُرَاتٞ سَآئِغٞ شَرَابُهُۥ وَهَٰذَا مِلۡحٌ أُجَاجٞۖ وَمِن كُلّٖ
تَأۡكُلُونَ لَحۡمٗا طَرِيّٗا وَتَسۡتَخۡرِجُونَ حِلۡيَةٗ تَلۡبَسُونَهَاۖ وَتَرَى ٱلۡفُلۡكَ فِيهِ مَوَاخِرَ لِتَبۡتَغُواْ
مِن فَضۡلِهِۦ وَلَعَلَّكُمۡ تَشۡكُرُونَ ١٢

**12.** ሁለት ባህሮች አይስተካከሉም ይህ ጣፋጭ፤ ጥምን ቆራጭ መጠጡ በገር ተዋጭ ነው። ይህኛው ደግሞ ጨው መርጋጋ ነው። ከሁሉም እርጥብ ስጋን ትበላላችሁ። የምትለብሷትንም ጌጥ ታወጣላችሁ። ከችሮታው ልትፈልጉና ልታመሰግኑም መርከቦችን በእርሱ ውስጥ ውሃውን ቀዳጆች ሆነው ሲንሻለሉ ታያለህ።

يُولِجُ ٱلَّيۡلَ فِى ٱلنَّهَارِ وَيُولِجُ ٱلنَّهَارَ فِى ٱلَّيۡلِ وَسَخَّرَ ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ كُلٌّ يَجۡرِى لِأَجَلٍ
مُّسَمًّىۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمۡ لَهُ ٱلۡمُلۡكُۚ وَٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ مَا يَمۡلِكُونَ مِن
قِطۡمِيرٍ ﴿١٣﴾ إِن تَدۡعُوهُمۡ لَا يَسۡمَعُواْ دُعَآءَكُمۡ وَلَوۡ سَمِعُواْ مَا ٱسۡتَجَابُواْ لَكُمۡۖ وَيَوۡمَ
ٱلۡقِيَٰمَةِ يَكۡفُرُونَ بِشِرۡكِكُمۡۚ وَلَا يُنَبِّئُكَ مِثۡلُ خَبِيرٍ ﴿١٤﴾

**13-14.** ሌሊትን በቀን ውስጥ ያስገባል፡፡ ቀንንም በሌሊት ውስጥ ያስገባል፡፡ ፀሀይንና ጨረቃንም ገራ፡፡ ሁሉም እስከ ተወሰነለት ጊዜ ድረስ ይሮጣሉ፡፡ ይህን የሚያደርገው ጌታችሁ አላህ ብቻ ነው፡፡ ንግስናው የእሱ ብቻ ነው፡፡ እነዚያም ከእርሱ ሌላ የምትገዟቸው የተምር ፍሬ ሽፋን* ያህል እንኳን አይኖራቸውም፡፡ ብትጠሩዋቸው ጥሪያችሁን አይሰሙም፡፡ ቢሰሙም ኖሮ ለእናንተ አይመልሱላችሁም፡፡ በትንሳዔም ቀን እነርሱን በአላህ ማጋራታችሁን ይክዳሉ፡፡ ለእናንተ እንደ ውስጠ አዋቂው አላህ ማንም አይነግርህም፡፡

* በአን-ኒሳእ ም. (49) ኛ በታች የተብራራውን መለስ ብለህ አንብብ፡፡

۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ أَنتُمُ ٱلۡفُقَرَآءُ إِلَى ٱللَّهِۖ وَٱللَّهُ هُوَ ٱلۡغَنِىُّ ٱلۡحَمِيدُ ﴿١٥﴾

**15.** እናንተ ሰዎች ሆይ፣ እናንተ ሁል ጊዜ ወደ አላህ ከጃዮች ናችሁ፡፡ አላህ እርሱ ተብቃቂና ምስጉን ነው፡፡

إِن يَشَأۡ يُذۡهِبۡكُمۡ وَيَأۡتِ بِخَلۡقٍ جَدِيدٍ ﴿١٦﴾ وَمَا ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ بِعَزِيزٍ ﴿١٧﴾

**16-17.** ቢሻ ያስወግዳችሁና አዲስን ፍጡር ያመጣል (ይፈጥራል)፡፡ ይህም በአላህ ላይ ምንም አስቸጋሪ አይደለም፡፡

وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٌ وِزۡرَ أُخۡرَىٰۚ وَإِن تَدۡعُ مُثۡقَلَةٌ إِلَىٰ حِمۡلِهَا لَا يُحۡمَلۡ مِنۡهُ شَىۡءٌ وَلَوۡ كَانَ ذَا
قُرۡبَىٰٓۗ إِنَّمَا تُنذِرُ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُم بِٱلۡغَيۡبِ وَأَقَامُواْ ٱلصَّلَوٰةَۚ وَمَن تَزَكَّىٰ فَإِنَّمَا يَتَزَكَّىٰ
لِنَفۡسِهِۦۚ وَإِلَى ٱللَّهِ ٱلۡمَصِيرُ ﴿١٨﴾

**18.** ኃጢአትን ተሸካሚይም ነፍስ የሌላውን ሸክም አትሸከምም፡፡ የራሷ ወንጀል የከበዳትም ነፍስ እርዳታ እንዲያደረግላት ብትጠራ ተጠሪው የቅርብ ዝምድና ባለቤት ቢሆንም እንኳን ከእርሷ አንድን ነገር የሚሸከምላት አታገኝም፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የምታስጠነቅቀው እነዚያን ጌታቸውን፤ በሩቅ የሚፈሩትን ሶላትንም አስተካክለው የሚሰገዱትን ብቻ ነው፡፡ ከወንጀል የተጥራራ ሰው ሁሉ የሚጥራራው ለራሱ ብቻ ነው፡፡ መመለሻውም ወደ አላህ ብቻ ነው፡፡

**ከፈጣሪ ምዕራፍ ከአንቀፅ (12-18) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የጌታን አንድነት ማረጋገጥ፤
2. የአላህን እውቀት፤ ጥበብና ችሎታ፤ ስፋትና ግዝፈት በግልፅ ማሳየት፤
3. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማጣራት፤
4. በዱንያም ሆነ በአኼራ ከአላህ በስተቀር ጣኦት፤ አማልክቶች አምላኪዎቻቸውን እንደማይጠቅሙ፤
5. የቂያማ ዕለት የአላህ ፊት ምን እንደሚመስል፤
6. የአላህ ምሉዕ ባህሪያቶች በጥቂቱ፤
7. የቂያማ ቀን ችግር ምን ያህል እንደሚከብድ፤
8. ከአላህ ቅጣት ማስጠንቀቅ ማስፈራራት ለማን እንደሚጠቅም፤
9. መልካም የሰራ ለራሱ እንደሆነ፤ መጥፎም የሰራ እንዲሁ ለራሱ ስለ መሆኑ፤
10. ይህ አንቀፅ በህዝቦች ዘንድ ምንም ፈጠራ የሚባል እንደሌለ ከሚያመለክቱት አናቅፅ አንዱ መሆኑን እንማራለን።

وَمَا يَسۡتَوِي ٱلۡأَعۡمَىٰ وَٱلۡبَصِيرُ ﴿١٩﴾ وَلَا ٱلظُّلُمَٰتُ وَلَا ٱلنُّورُ ﴿٢٠﴾ وَلَا ٱلظِّلُّ
وَلَا ٱلۡحَرُورُ ﴿٢١﴾ وَمَا يَسۡتَوِي ٱلۡأَحۡيَآءُ وَلَا ٱلۡأَمۡوَٰتُۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُسۡمِعُ مَن يَشَآءُۖ
وَمَآ أَنتَ بِمُسۡمِعٖ مَّن فِي ٱلۡقُبُورِ ﴿٢٢﴾

**19-22.** እውርና የሚያይ ጨለማና ብርሃን፤ ጥላና ሐሩር፤ ህያውና ሙታንም እንደዚሁ አይስተካከሉም። አላህ የሚሻውን ሰው ያሰማል። አንተ ግን በመቃብር ውስጥ ያሉትን አሰሚ አይደለህም። አንተ አስጠንቃቂ እንጂ ሌላ አይደለህም።

إِنۡ أَنتَ إِلَّا نَذِيرٌ ﴿٢٣﴾ إِنَّآ أَرۡسَلۡنَٰكَ بِٱلۡحَقِّ بَشِيرٗا وَنَذِيرٗاۚ وَإِن مِّنۡ أُمَّةٍ إِلَّا خَلَا فِيهَا
نَذِيرٞ ﴿٢٤﴾ وَإِن يُكَذِّبُوكَ فَقَدۡ كَذَّبَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ جَآءَتۡهُمۡ رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ وَبِٱلزُّبُرِ
وَبِٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡمُنِيرِ ﴿٢٥﴾ ثُمَّ أَخَذۡتُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۖ فَكَيۡفَ كَانَ نَكِيرِ ﴿٢٦﴾

**23-26.** እኛ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን በእውነት መምሪያ ላክንህ። ማንኛይቱም ህዝብ በውስጧ አስፈራሪ ያላለፈባት የለችም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢያስተባብሉህም ከእነዚህ ከበፊታቸው የነበሩትም ህዝቦች በእርግጥ ነብያትን አስተባብለዋል። መልዕክተኞቻቸው በግልፅ ማስረጃዎች በፁሁፎችም አብራሪ በሆነ መጽሐፍም መጥተዋቸዋል። ከዚያ እነዚያን የካዱትን ቀጣኋቸው። ቅጣቴም እንዴት ነበር (በስፍራው ነው ተገቢ ነው)።

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءً فَأَخْرَجْنَا بِهِۦ ثَمَرَٰتٍ مُّخْتَلِفًا أَلْوَٰنُهَا ۚ وَمِنَ ٱلْجِبَالِ
جُدَدٌۢ بِيضٌ وَحُمْرٌ مُّخْتَلِفٌ أَلْوَٰنُهَا وَغَرَابِيبُ سُودٌ ﴿٢٧﴾ وَمِنَ ٱلنَّاسِ وَٱلدَّوَآبِّ وَٱلْأَنْعَٰمِ
مُخْتَلِفٌ أَلْوَٰنُهُۥ كَذَٰلِكَ ۗ إِنَّمَا يَخْشَى ٱللَّهَ مِنْ عِبَادِهِ ٱلْعُلَمَٰٓؤُا۟ ۗ إِنَّ ٱللَّهَ عَزِيزٌ غَفُورٌ ﴿٢٨﴾

**27-28.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከሰማይ ውሃን ማውረዱን አላየህምን? በእርሱም ዓይነቶቻቸው የተለያዩ ፍሬዎችን አወጣን። ከጋራዎችም መልካቸው የተለዩ ነጮች፤ ቀዮች፤ በጣም ጥቁሮችም የሆኑ መንገዶች አሉ። ከሰዎችም ከተንቀሳቃሾችና ከቤት እንስሳዎችም እንደዚሁ መልኮቻቸው የተለያየ አሉ። አላህን ከባሮቹ ውስጥ የሚፈሩት አዋቂዎች ብቻ ናቸው። አላህ አሸናፊና መሃሪ ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَتْلُونَ كِتَٰبَ ٱللَّهِ وَأَقَامُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَنفَقُوا۟ مِمَّا رَزَقْنَٰهُمْ سِرًّا وَعَلَانِيَةً يَرْجُونَ
تِجَٰرَةً لَّن تَبُورَ ﴿٢٩﴾ لِيُوَفِّيَهُمْ أُجُورَهُمْ وَيَزِيدَهُم مِّن فَضْلِهِۦٓ ۚ إِنَّهُۥ غَفُورٌ شَكُورٌ ﴿٣٠﴾

**29-30.** እነዚያ የአላህን መጽሐፍ የሚያነቡ ሶላትን አስተካክለው ያደረሱ ከሰጠናቸውም ሲሳይ በምስጢርም ሆነ በግልፅ የለገሱ የማትከስርን ንግድ ተስፋ ያደርጋሉ። ምንዳዎቻቸውን ሊሞላላቸው ከችሮታውም ሊጨምርላቸው ተስፋ ያደርጋሉ። እርሱ በጣም መሃሪ፤ አመስጋኝ ነውና።

وَٱلَّذِىٓ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ مِنَ ٱلْكِتَٰبِ هُوَ ٱلْحَقُّ مُصَدِّقًا لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ ۗ
إِنَّ ٱللَّهَ بِعِبَادِهِۦ لَخَبِيرٌۢ بَصِيرٌ ﴿٣١﴾

**31.** ያ ከመጽሐፉ ወደ አንተ ያወረድነው ከበፊቱ ላለው አረጋጋጭ ሲሆን እርሱ እውነት ነው። አላህ በእርግጥ የባሮቹን ውስጥ አዋቂና ተመልካች ነው።

ثُمَّ أَوْرَثْنَا ٱلْكِتَٰبَ ٱلَّذِينَ ٱصْطَفَيْنَا مِنْ عِبَادِنَا ۖ فَمِنْهُمْ ظَالِمٌ لِّنَفْسِهِۦ وَمِنْهُم مُّقْتَصِدٌ
وَمِنْهُمْ سَابِقٌۢ بِٱلْخَيْرَٰتِ بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلْفَضْلُ ٱلْكَبِيرُ ﴿٣٢﴾ جَنَّٰتُ عَدْنٍ يَدْخُلُونَهَا
يُحَلَّوْنَ فِيهَا مِنْ أَسَاوِرَ مِن ذَهَبٍ وَلُؤْلُؤًا ۖ وَلِبَاسُهُمْ فِيهَا حَرِيرٌ ﴿٣٣﴾ وَقَالُوا۟ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ
ٱلَّذِىٓ أَذْهَبَ عَنَّا ٱلْحَزَنَ ۖ إِنَّ رَبَّنَا لَغَفُورٌ شَكُورٌ ﴿٣٤﴾ ٱلَّذِىٓ أَحَلَّنَا دَارَ ٱلْمُقَامَةِ مِن فَضْلِهِۦ
لَا يَمَسُّنَا فِيهَا نَصَبٌ وَلَا يَمَسُّنَا فِيهَا لُغُوبٌ ﴿٣٥﴾

**32-35.** ከዚያ እነዚያ ከባሮቻችን የመረጥናቸውን መጽሐፉን አወረስናቸው ከእነርሱም ነፍሱን በዳይ አለ ከእነርሱም መካከለኛ አለ ከእነርሱም በአላህ ፈቃድ በበጎ ስራዎች ቀዳሚ አለ ያ ማውረስ እርሱ ታላቅ ችሮታ ነው። የመኖሪያ ገነቶችን በውስጧ የወርቅ አንባሮችን ሉልንም የሚሸለሙ ሆነው ይገቡበታል። በእርሷ ውስጥ አልባሳታቸውም ሀር ነው። ይላሉም ምስጋና ሁሉ ለዚያ ከእኛ ላይ ሐዘንን፤ ላስወገደልን አላህ ይገባው። አላህ ጌታችን በጣም መሃሪና አመስጋኝ ነውና። እርሱም ያ ከችሮታው የዘላለም መኖሪያን አገር ያሰፈረን ነው። በእርሷም ውስጥ መከራ አይነካንም በእርሷም ውስጥ ድካም አይነካንም።

وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَهُمْ نَارُ جَهَنَّمَ لَا يُقْضَىٰ عَلَيْهِمْ فَيَمُوتُواْ وَلَا يُخَفَّفُ عَنْهُم مِّنْ عَذَابِهَاۚ
كَذَٰلِكَ نَجْزِي كُلَّ كَفُورٖ ٣٦ وَهُمْ يَصْطَرِخُونَ فِيهَا رَبَّنَآ أَخْرِجْنَا نَعْمَلْ صَٰلِحًا غَيْرَ ٱلَّذِي
كُنَّا نَعْمَلُۚ أَوَلَمْ نُعَمِّرْكُم مَّا يَتَذَكَّرُ فِيهِ مَن تَذَكَّرَ وَجَآءَكُمُ ٱلنَّذِيرُۖ فَذُوقُواْ فَمَا لِلظَّٰلِمِينَ
مِن نَّصِيرٍ ٣٧ إِنَّ ٱللَّهَ عَٰلِمُ غَيْبِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِۚ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٣٨

**36-38.** እነዚያ በአላህ የካዱት ለእነርሱ የገሀነም እሳት አለላቸው። ይሞቱ ዘንድ በእነርሱ ላይ በሞት አይፈረድም። ከቅጣቷም ከእነርሱ አይቀልላቸውም። እንደዚሁ ከሓዲያንን ሁሉ እንመነዳለን። እነርሱም በእርሷ ውስጥ እርዳታን በመፈለግ በኃይል ይጮሃሉ። ጌታችን ሆይ! ከዚያ እንሰራው ከነበረው ሌላ በጎ ስራን እንሰራ ዘንድ አውጣን ይላሉ። በእርሱ ውስጥ ያስታወሰ ሰው የሚገሰፅበትን እድሜ አላቆየናችሁምን? አስጠንቃቂውም መጥቶላችኋል። አስተባብላችኋልም ስለዚህ ቅመሱ ለበደለኞችም ምንም ረዳት የላቸውም ይባላሉ። አላህ የሰማያትንና የምድርን ምስጢር በእርግጥ አዋቂ ነው። እርሱ በልቦች ውስጥ ያለን ሁሉ አዋቂ ነውና።

هُوَ ٱلَّذِي جَعَلَكُمْ خَلَٰٓئِفَ فِي ٱلْأَرْضِۚ فَمَن كَفَرَ فَعَلَيْهِ كُفْرُهُۥۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلْكَٰفِرِينَ
كُفْرُهُمْ عِندَ رَبِّهِمْ إِلَّا مَقْتًاۖ وَلَا يَزِيدُ ٱلْكَٰفِرِينَ كُفْرُهُمْ إِلَّا خَسَارًا ٣٩

**39.** (ሰዎች ሆይ!) እርሱ ያ በምድር ውስጥ ምትኮች ያደረጋችሁ ነው። የካደም ሰው ክህደቱ በእርሱው ላይ ብቻ ነው። ከሓዲያን ም ክህደታቸው ከጌታቸው ዘንድ መጠላትን እንጂ ሌላ አይጨምርላቸውም።

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ شُرَكَآءَكُمُ ٱلَّذِينَ تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَرُونِي مَاذَا خَلَقُواْ مِنَ ٱلۡأَرۡضِ أَمۡ لَهُمۡ شِرۡكٞ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ أَمۡ ءَاتَيۡنَٰهُمۡ كِتَٰبٗا فَهُمۡ عَلَىٰ بَيِّنَتٖ مِّنۡهُۚ بَلۡ إِن يَعِدُ ٱلظَّٰلِمُونَ بَعۡضُهُم بَعۡضًا إِلَّا غُرُورًا ﴿٤٠﴾ ۞ إِنَّ ٱللَّهَ يُمۡسِكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ أَن تَزُولَاۚ وَلَئِن زَالَتَآ إِنۡ أَمۡسَكَهُمَا مِنۡ أَحَدٖ مِّنۢ بَعۡدِهِۦٓۚ إِنَّهُۥ كَانَ حَلِيمًا غَفُورٗا ﴿٤١﴾

**40-41.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያን ከአላህ ሌላ የምትገዟቸውን ተጋሪዎቻችሁ አያችሁን? ከምድር ምንን እንደ ፈጠሩ አሳዩኝ ወይስ ለእነርሱ በሰማያት ውስጥ ሽርክና አላቸውን? ወይስ መጽሐፍን ሰጠናቸውና እነርሱ ከርሱ በግልጽ አስረጅ ላይ ናቸውን? አይደለም በደለኞች ከፊላቸው ከፊሉን ማታለልን እንጂ አይቀጥሩም በላቸው። አላህ ሰማያትንና ምድርን እንዳይወገዱ ይይዛቸዋል።* ቢወገዱም ከእርሱ ሌላ አንድም የሚይዛቸው የለም። እነሆ እርሱ ታጋሽና መሃሪ ነውና።

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል። «አላህ ምድርን በእጁ ይዞ በቀኝ እጁ ደግሞ ሰማያትን ይጠቀልልና «እኔ ንጉስ ነኝ! የምድር ነገስታት የታሉ?» ይላል።» ይህና ይህን መሰል የአላህን ባህሪና ስሞች የሚናገሩ የቁርአን አናቅጾችና ሐዲሶች ተፍሲር በተመለከተ አላህን ከማንም ከምንም ፍጡር ጋር ሳናመሳስልና አላህን ከጉድለት በማጥራት በሰለፎች ግንዛቤና አረዳድ እናስቀምጣለን እዚህ ላይ በጣም ልንጠነቀቅ የሚገባው ነገር ፣ኛ እንዴት? (ከይፍ?) እና ለምን? የሚሉ ጥያቄዎች ሁሉ በፍጹም የተከለከሉ ናቸው 2ኛ አላህ በማንም በምንም አይመሳሰልም በዚህ ዙሪያ በሰፊው ለመረዳት በሱረቱ አል አዕራፍ (54)
አንቀጽ ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ ተመልከት።

وَأَقۡسَمُواْ بِٱللَّهِ جَهۡدَ أَيۡمَٰنِهِمۡ لَئِن جَآءَهُمۡ نَذِيرٞ لَّيَكُونُنَّ أَهۡدَىٰ مِنۡ إِحۡدَى ٱلۡأُمَمِۖ فَلَمَّا جَآءَهُمۡ نَذِيرٞ مَّا زَادَهُمۡ إِلَّا نُفُورًا ﴿٤٢﴾ ٱسۡتِكۡبَارٗا فِي ٱلۡأَرۡضِ وَمَكۡرَ ٱلسَّيِّيِٕۚ وَلَا يَحِيقُ ٱلۡمَكۡرُ ٱلسَّيِّئُ إِلَّا بِأَهۡلِهِۦۚ فَهَلۡ يَنظُرُونَ إِلَّا سُنَّتَ ٱلۡأَوَّلِينَۚ فَلَن تَجِدَ لِسُنَّتِ ٱللَّهِ تَبۡدِيلٗاۖ وَلَن تَجِدَ لِسُنَّتِ ٱللَّهِ تَحۡوِيلًا ﴿٤٣﴾

**42-43.** አስፈራሪም ቢመጣላቸው ከህዝቦች ሁሉ ከአንደኛዋ ይበልጥ የተመሩ ሊሆኑ የመሃላቸውን ዲካ አድርሰው በአላህ ማሉ። አስፈራሪም በመጣላቸው ጊዜ መበርገግን እንጂ ሌላ አልጨመረላቸውም። በምድር ላይ ኩራትንና በክፉ ተንኮል መዶለትንም እንጂ አልጨመረላቸውም። ክፉ ተንኮልም በባለቤቱ ላይ እንጂ በሌላ ላይ አይሰፍርም። የቀድሞዎቹን ደንብ እንጂ ይጠብቃሉን? ለአላህ ደንብም መለወጥን አታገኝም ለአላህ ደንብም መዛወርን (መቀየር) አታገኝም።

أَوَلَمْ يَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَيَنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَـٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ
وَكَانُوٓا۟ أَشَدَّ مِنْهُمْ قُوَّةًۭ ۚ وَمَا كَانَ ٱللَّهُ لِيُعْجِزَهُۥ مِن شَىْءٍۢ فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ
وَلَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ إِنَّهُۥ كَانَ عَلِيمًۭا قَدِيرًۭا ﴿٤٤﴾

**44.** በምድር ላይ አይሄዱምና የእነዚያን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ሰዎች መጨረሻ እንዴት እንደ ነበረ አይመለከቱምን? ከእነርሱም በኃይል የበረቱ ነበሩ። አላህም በሰማያትም ሆነ በምድር ውስጥ ምንም ነገር የሚያቅተው አይደለም። እርሱ አዋቂ፤ ቻይ ነውና።

وَلَوْ يُؤَاخِذُ ٱللَّهُ ٱلنَّاسَ بِمَا كَسَبُوا۟ مَا تَرَكَ عَلَىٰ ظَهْرِهَا مِن دَآبَّةٍۢ
وَلَـٰكِن يُؤَخِّرُهُمْ إِلَىٰٓ أَجَلٍۢ مُّسَمًّۭى ۖ فَإِذَا جَآءَ أَجَلُهُمْ
فَإِنَّ ٱللَّهَ كَانَ بِعِبَادِهِۦ بَصِيرًۢا ﴿٤٥﴾

**45.** አላህ ሰዎችን በሰሩት ኃጢአት ሁሉ ቢይዝ (ቢቀጣ) ኖሮ በምድር ወለል ላይ ምንንም ተንቀሳቃሽ ባልተወ ነበር። ግን እስከ ተወሰነ ጊዜ ድረስ ያቆያቸዋል። ጊዜያቸውም በመጣ ወቅት በኃጢአታቸው ይቀጣቸዋል። አላህ በባሮቹ ሁኔታ ሁሉ ተመልካች ነውና።

**ከፈጣሪ ምዕራፍ ከአንቀፅ (19-45) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ለትምህርት ምሳሌዎች መጥቀስ ጠቃሚ ስለመሆኑ፤
2. ከሓዲያን እውሮችና ሙታን ስለመሆናቸው፤
3. የነብዩ (ﷺ) ነብይነትን ማረጋገጥ፤
4. ዳኢዎችን ማፅናናት፤
5. ከሓዲያን አላህ በየጊዜው ለጥፋታቸው መታረሚያ የሚሆን ቅጣት ይልክባቸው እንደነበር፤
6. የፍጡሮቹን መልክ አቅምና ባህሪ በማቀያየሩ የአላህን ኃያልነት እንደሚገልፅ፤
7. እውቀት ለአላህ ፍራቻ ዋና መንገድ ስለመሆኑ፤
8. ቁርአን መቅራት፤ ሶላትን መስገድ፤ ዘካን መስጠትና ልዩ ልዩ ሰደቃዎችን መስጠት ተገቢ ስለመሆኑ፤
9. ሰዎች እንዲቶብቱ የአላህን መሀሪነት መግለፅ፤
10. ቁርአንን ያለምርምርም ቢሆን መቅራት መጠነኛ ምንዳ እንዳለው
11. የገሀነም ቅጣት ምን ያህል መራራ እንደሆነ መግለፅ፤
12. አርባ ዓመት የደረሰው ሰው ኃጢአት ለመስራት አላህ ዘንድ ምንም ማመካኛ እንደሌለው፤
13. ከሃዲ ዘላለም እንደሚቀጣ፤
14. ህዝቦች እየተተካኩ እንደሚኖሩ፤

15. በክህደት ላይ መቀጠል ከአላህ ራህመት እንደሚያርቅ፤
16. ሽርክን አውግዞ ተውሒድን ማፅደቅ፤
17. አጋሪዎች ለማጋራታቸው ምንም አይነት ማስረጃ እንደሌላቸው፤
18. አላህ ላባሮቹ ያለውን እዝነት፤
19. የአጋሪዎችን ቅጥፈትና ነውረኝነት፤
20. ተንኮል ፈፃሚው ይበልጥ እንደሚያሰጋው
21. በምድር ላይ ለመማር መጓዝ ተገቢ ስለመሆኑ፤
22. አላህ ምንም ነገር የማይሳነው መሆኑን፤
23. ቅጣትን አምጣ እያለ ማፋጠን አስፈላጊ እንደልሆነ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የፈጣሪ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (36)
# የያሲን ምዕራፍ
## (ሱረቱ ያሲን)

سُورَةُ يسٓ

### በመካ ነው የወረደው። የአናቅፅ ብዛት (83) ናቸው።
### የሱረቱ ያሲን መግቢያ

ነብዮ (ﷺ) ከመልዕክተኞቹ አንዱ ለመሆናቸው በመሀላ አጠናክሮ ከማረጋገጡም በተጨማሪ በትክክለኛ መንገድ መሆኑንም ይገልፃል። የቁርኣን መውረድ ዋናው ምክንያቱም ከእነሱ በፊት የነበሩ ሰዎች ያልሰሙትን ማስፈራራቱ የማይጠቅማቸው ሰዎች እንዳሉም ገልፆ ማስፈራራት የሚጠቅመው ቁርኣንን ለመቀበል ለተዘጋጁና አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ብቻ መሆኑን ያሳስባል። ለመካ ሰዎች ምሳሌን በመጥቀስ በአስተማሪዎችና በአስተባባዮች መካከል ያለውን ይገልፃል የሁለቱንም መጨረሻ ይናገራል። የአላህን ሀያልነት የሰዎች መጨረሻም ምን እንደሚመስል በማስተማር መልዕክቱን ያካትታል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يسٓ ١

**1.** ያሲን፤* (የዚህን ቃል ትርጉም አላህ ያውቃል)።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፲ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَٱلۡقُرۡءَانِ ٱلۡحَكِيمِ ٢ إِنَّكَ لَمِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ٣ عَلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٤
تَنزِيلَ ٱلۡعَزِيزِ ٱلرَّحِيمِ ٥ لِتُنذِرَ قَوۡمٗا مَّآ أُنذِرَ ءَابَآؤُهُمۡ فَهُمۡ غَٰفِلُونَ ٦

**2-6.** (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ በእርግጥ በቀጥታው መንገድ ላይ ከሆኑት መልዕክተኞች መካከል አንዱ ነህ ብየ ጥበብ በተሞላበት ቁርኣን እምላለሁ። ቁርኣን አሸናፊና አዛኝ ከሆነው አምላክ ከአላህ መወረድን ተወረደ። (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) አባቶቻቸው ያልተስፈራሩትን ህዝቦች ልታስጠነቅቅበት ቁርኣን ተወረደ። እነርሱ ዘንጊዎች ናቸውና።

لَقَدۡ حَقَّ ٱلۡقَوۡلُ عَلَىٰٓ أَكۡثَرِهِمۡ فَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ٧ إِنَّا جَعَلۡنَا فِيٓ أَعۡنَٰقِهِمۡ أَغۡلَٰلٗا فَهِيَ إِلَى
ٱلۡأَذۡقَانِ فَهُم مُّقۡمَحُونَ ٨ وَجَعَلۡنَا مِنۢ بَيۡنِ أَيۡدِيهِمۡ سَدّٗا وَمِنۡ خَلۡفِهِمۡ سَدّٗا فَأَغۡشَيۡنَٰهُمۡ

فَهُمْ لَا يُبْصِرُونَ ﴿٩﴾ وَسَوَآءٌ عَلَيْهِمْ ءَأَنذَرْتَهُمْ أَمْ لَمْ تُنذِرْهُمْ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿١٠﴾ إِنَّمَا تُنذِرُ
مَنِ ٱتَّبَعَ ٱلذِّكْرَ وَخَشِىَ ٱلرَّحْمَٰنَ بِٱلْغَيْبِ ۖ فَبَشِّرْهُ بِمَغْفِرَةٍ وَأَجْرٍ كَرِيمٍ ﴿١١﴾

**7-11.** በአብዛኞቻቸቸው ላይ ቃሉ በእውነት ተረጋገጠ፡፡ ስለዚህ እነርሱ አያምኑም፡፡ እኛ በአንገቶቻቸው ላይ እንዛዝላዎችን አደረግን፡፡ እሷም (እንዛዝላይቱም) ወደ አገጮቻቸው ደራሽ ናት፡፡ ከዚያ እነርሱ ራሶቻቸውን ያንጋጠጡ ናቸው፡፡ ከበስተፊታቸውም ግርዶን ከበስተኋላቸውም ግርዶን አደረግንና ሸፈንናቸው፡፡ ስለዚህ እነርሱ አያዩም፡፡ ብታስጠነቅቃቸውም ባታስጠነቅቃቸውም ለእነርሱ ሁሉም እኩል ነው፡፡ (ምንም ለውጥ አያመጣም) አያምኑምና፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የምታስጠነቅቀው ግሳጼን የተከተለንና አልረህማንን በሩቅ የፈራን ሰው ብቻ ነው፡፡ እናም በምህረትና በመልካም ምንዳ አብስረው፡፡

إِنَّا نَحْنُ نُحْىِ ٱلْمَوْتَىٰ وَنَكْتُبُ مَا قَدَّمُوا۟ وَءَاثَٰرَهُمْ ۚ وَكُلَّ شَىْءٍ أَحْصَيْنَٰهُ فِىٓ إِمَامٍ مُّبِينٍ ﴿١٢﴾

**12.** እኛ ሙታንን እኛ በእርግጥ ህያው እናደርጋለን፡፡ ያስቀደሙትንም ስራ ፍለጎቻቸውንም እንጽፋለን፡፡ ሁሉን ነገር ገላጭና መሪ በሆነ መጽሐፍ ውስጥ አጠቃለልነው፡፡

وَٱضْرِبْ لَهُم مَّثَلًا أَصْحَٰبَ ٱلْقَرْيَةِ إِذْ جَآءَهَا ٱلْمُرْسَلُونَ ﴿١٣﴾ إِذْ أَرْسَلْنَآ إِلَيْهِمُ ٱثْنَيْنِ فَكَذَّبُوهُمَا
فَعَزَّزْنَا بِثَالِثٍ فَقَالُوٓا۟ إِنَّآ إِلَيْكُم مُّرْسَلُونَ ﴿١٤﴾ قَالُوا۟ مَآ أَنتُمْ إِلَّا بَشَرٌ مِّثْلُنَا وَمَآ أَنزَلَ ٱلرَّحْمَٰنُ
مِن شَىْءٍ إِنْ أَنتُمْ إِلَّا تَكْذِبُونَ ﴿١٥﴾ قَالُوا۟ رَبُّنَا يَعْلَمُ إِنَّآ إِلَيْكُمْ لَمُرْسَلُونَ ﴿١٦﴾ وَمَا عَلَيْنَآ إِلَّا
ٱلْبَلَٰغُ ٱلْمُبِينُ ﴿١٧﴾ قَالُوٓا۟ إِنَّا تَطَيَّرْنَا بِكُمْ ۖ لَئِن لَّمْ تَنتَهُوا۟ لَنَرْجُمَنَّكُمْ وَلَيَمَسَّنَّكُم مِّنَّا عَذَابٌ
أَلِيمٌ ﴿١٨﴾ قَالُوا۟ طَٰٓئِرُكُم مَّعَكُمْ ۚ أَئِن ذُكِّرْتُم ۚ بَلْ أَنتُمْ قَوْمٌ مُّسْرِفُونَ ﴿١٩﴾

**13-19.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነርሱም የከተማይቱን (የእንጣኪያን) ሰዎች ምሳሌ መልዕክተኞች በመጧት ጊዜ የሆነውን ግለጽላቸው፡፡ ወደ እነርሱ ሁለትን ሰዎች በላክንና ባስተባበሉዋቸው ጊዜ በሶስተኛም በአበረታናቸውና እኛ ወደ እናንተ መልክተኞች ነን ባሏቸው ጊዜ የሆነውን ምሳሌ ግለጽላቸው፡፡ እናንተ መሰላችን ሰዎች እንጂ ሌላ አይደላችሁም፡፡ አልረህማንም ምንንም ነገር አላወረደም፡፡ እናንተ የምትዋሹ እንጂ ሌላ አይደላችሁም አሉዋቸው፡፡ መልዕክተኞችም ጌታችን ያውቃል

እኛ ወደ እናንተ በእርግጥ መልክተኞች ነን። በእኛ ላይም ግልፅ የሆነ ማድረስ እንጂ ሌላ የለብንም አሉ። ህዝቦቹም እኛ በእናንተ ገደ ቢሶች ሆነ። ከዚህ ሰበካችሁ ባትከለክሉ በእርግጥ እንወግራችኋለን። ከእኛም አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ ያገኛችኋል አሉ። ገደ ቢስነታችሁ ከናንተው ጋር ነው። ብትገሰጹ (ትዝታላችሁን?) በእውነቱ እናንተ «ወሰን አላፊ ህዝቦች ናችሁ»አሏቸው።

وَجَآءَ مِنۡ أَقۡصَا ٱلۡمَدِينَةِ رَجُلٞ يَسۡعَىٰ قَالَ يَٰقَوۡمِ ٱتَّبِعُواْ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ٢٠ ٱتَّبِعُواْ مَن
لَّا يَسۡـَٔلُكُمۡ أَجۡرٗا وَهُم مُّهۡتَدُونَ ٢١ وَمَالِيَ لَآ أَعۡبُدُ ٱلَّذِي فَطَرَنِي وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ٢٢
ءَأَتَّخِذُ مِن دُونِهِۦٓ ءَالِهَةً إِن يُرِدۡنِ ٱلرَّحۡمَٰنُ بِضُرّٖ لَّا تُغۡنِ عَنِّي شَفَٰعَتُهُمۡ شَيۡـٔٗا
وَلَا يُنقِذُونِ ٢٣ إِنِّيٓ إِذٗا لَّفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ٢٤ إِنِّيٓ ءَامَنتُ بِرَبِّكُمۡ فَٱسۡمَعُونِ ٢٥ قِيلَ
ٱدۡخُلِ ٱلۡجَنَّةَۖ قَالَ يَٰلَيۡتَ قَوۡمِي يَعۡلَمُونَ ٢٦ بِمَا غَفَرَ لِي رَبِّي وَجَعَلَنِي مِنَ ٱلۡمُكۡرَمِينَ ٢٧

**20-27.** ከከተማይቱም ሩቅ ዳርቻ የሚሮጥ ሰው መጣ። ወገኖቼ ሆይ! መልዕክተኞቹን ተከተሉ አለ። እነርሱ ቅኑን መንገድ የተመሩ ሲሆን ክፍያን የማይጠይቋችሁን ሰዎች ተከተሉ አላቸው። ያንንም የፈጠረኝንና ወደ እርሱም የምትመለሱበትን ጌታ የማልገዛበት ለእኔ ምን ምክንያት አለኝ አለ። ከእርሱ ሌላ አማልክትን እይዛለሁን? አልራህማን ሊጎዳኝ ቢፈልግ ምልጃቸው ከእኔ (ለመመለስ) ምንም አትጠቅመኝም አያድኑኝምም። እኔ ያን ጌዜ በግልፅ ስህተት ውስጥ ነኝ። እኔ በጌታችሁ አመንኩ። ስሙኝም አለ። ገነትን ግባ ተባለ። እርሱም አለ ወገኖቼ ቢያውቁ* እመኛለሁ። ጌታዬ ለእኔ ምህረት ያደረገልኝና ከተከበሩትም ያደረገኝ መሆኑን።

* (ሀ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «የእኔንና እኔ የተላኩበት መልዕክት ምሳሌ ልክ እንድ ሰው ወደ ሰዎች መጥቶ «የጠላት ኃይልን በአይኖቼ ተመልክቻለሁ ራሳችሁን እንድትጠብቁ አስጠነቅቃችኋለሁ» ሲላቸው የተወሰኑት ሰምተውት በለሊት ተደብቀው ቀስ ብለው በመጓዝ ደህና ሲሆኑ የተወሰኑት ግን ሰውየውን አላመኑትም ስለዚህ ጠላት ጠዋት መጥቶ ማረካቸውና ሁሉንም አጠፋቸው።»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) በሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «በአላህ መንገድ ላይ መስዋእት ከሆነ ሰው በስተቀር ማንኛውም ወደ ጀነት የሚገባ ሰው በምድር ላይ ያሉት ነገሮች ቢያገኝ ወደ ምድር መመለስን ይፈልጋል። ዳሩ ግን መስዋእት የሆነ ሰው በአላህ ዘንድ ከሚያገኘው ክብር የተነሳ ወደ ምድር ተመልሶ በአላህ መንገድ ላይ መገደልን ይመኛል።»

(ሐ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ (የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ሰዎች ሆይ! ጀነትን ከሰይፍ ጥላ ስር እንደሆነች እወቁ።»

(መ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ይሉ ነበር፡- «ጌታዬ ሆይ! እኔ አቅም ከማጣት፤ ከስንፍና፤ ከፍርሃትና በእርጅና መጃጃት ባንተ እጠበቃለሁ። እንዲሁም በሕይወትና ከመሞት ፈተናዎችና ከቀብር ቅጣት ባንተ እጠበቃለሁ።»

(ሠ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሰው በአንድ መቶ ግመሎች መካከል ለግልቢያ ምቹ የሆነውን ግመል ለመምረጥ እንደሚያስቸግረው ሰዎችም እንደ ግመሎች ናቸው።»

۞وَمَآ أَنزَلۡنَا عَلَىٰ قَوۡمِهِۦ مِنۢ بَعۡدِهِۦ مِن جُندٖ مِّنَ ٱلسَّمَآءِ وَمَا كُنَّا مُنزِلِينَ ٢٨ إِن كَانَتۡ
إِلَّا صَيۡحَةٗ وَٰحِدَةٗ فَإِذَا هُمۡ خَٰمِدُونَ ٢٩ يَٰحَسۡرَةً عَلَى ٱلۡعِبَادِۚ مَا يَأۡتِيهِم مِّن رَّسُولٍ
إِلَّا كَانُواْ بِهِۦ يَسۡتَهۡزِءُونَ ٣٠ أَلَمۡ يَرَوۡاْ كَمۡ أَهۡلَكۡنَا قَبۡلَهُم مِّنَ ٱلۡقُرُونِ أَنَّهُمۡ إِلَيۡهِمۡ
لَا يَرۡجِعُونَ ٣١ وَإِن كُلّٞ لَّمَّا جَمِيعٞ لَّدَيۡنَا مُحۡضَرُونَ ٣٢

**28-32.** ከእርሱም በኋላ በህዝቦቹ ላይ ልናጠፋቸው ሰራዊትን ከሰማይ አላወረድንም በማንም ላይ አውራጆችም አልነበርንም። ቅጣታቸው አንዲት ጩኸት እንጂ ሌላ አልነበረችም። ወዲያውኑም እነርሱ ጠፊዎች ሆኑ። በባሮቹ ላይ ዋ፣ ቁጭት፣ ከመልዕክተኛ አንድም አይመጣላቸውም በርሱ ያፌዙበት ቢሆን እንጂ ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች ብዙዎችን ማጥፋታችንንና እነርሱ ወደ እነርሱ የማይመለሱ መሆናቸውን አላወቁምን? ሁሉም እኛ ዘንድ (የሚሰበሰቡ) የሚቀረቡ እንጂ ሌላ አይደሉም።

وَءَايَةٞ لَّهُمُ ٱلۡأَرۡضُ ٱلۡمَيۡتَةُ أَحۡيَيۡنَٰهَا وَأَخۡرَجۡنَا مِنۡهَا حَبّٗا فَمِنۡهُ يَأۡكُلُونَ ٣٣ وَجَعَلۡنَا فِيهَا
جَنَّٰتٖ مِّن نَّخِيلٖ وَأَعۡنَٰبٖ وَفَجَّرۡنَا فِيهَا مِنَ ٱلۡعُيُونِ ٣٤ لِيَأۡكُلُواْ مِن ثَمَرِهِۦ وَمَا عَمِلَتۡهُ
أَيۡدِيهِمۡۚ أَفَلَا يَشۡكُرُونَ ٣٥ سُبۡحَٰنَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلۡأَزۡوَٰجَ كُلَّهَا مِمَّا تُنۢبِتُ ٱلۡأَرۡضُ وَمِنۡ
أَنفُسِهِمۡ وَمِمَّا لَا يَعۡلَمُونَ ٣٦

**33-36.** የሞተችውም ምድር ለእነርሱ ምልክት ናት። ህያው አደረግናት። ከእሷ ፍሬን አወጣን ከእሱም ይበላሉ። በእሷ ውስጥ ከዘምባባዎችና ከወይኖች የሆኑ አትክልቶችን አደረግን። በእርሷም ውስጥ ምንጮችን አፈለቅን። ከፍሬውና እጆቻቸው ከሰሩትም ይበሉ ዘንድ ይህን አደረግን። አያመሰግኑምን? ያ፣ ምድር ከምታበቅለው፤ ወንዴንና ሴቴን ከነፍሶቻቸውም ከማያውቁትም ነገር (ዓይነቶችን) ሁሏንም ያ የፈጠረ (አምላክ) ጥራት ይገባው።

وَءَايَةٞ لَّهُمُ ٱلَّيۡلُ نَسۡلَخُ مِنۡهُ ٱلنَّهَارَ فَإِذَا هُم مُّظۡلِمُونَ ﴿٣٧﴾
وَٱلشَّمۡسُ تَجۡرِي لِمُسۡتَقَرّٖ لَّهَاۚ ذَٰلِكَ تَقۡدِيرُ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡعَلِيمِ ﴿٣٨﴾

**37-38.** ለሊቱም ለእነርሱ ምልክት ነው። ከእርሱ ላይ ቀንን አንገፋለን። ወዲያውኑም እነርሱ በጨለማ ውስጥ ይገባሉ። ፀሐይም ለእርሷ ወደ ሆነው መርጊያ ትሮጣለች። ይህ የአሸናፊውና የአዋቂው አምላክ የአላህ ውሳኔ ነው።

وَٱلۡقَمَرَ قَدَّرۡنَٰهُ مَنَازِلَ حَتَّىٰ عَادَ كَٱلۡعُرۡجُونِ ٱلۡقَدِيمِ ﴿٣٩﴾ لَا ٱلشَّمۡسُ يَنۢبَغِي لَهَآ أَن تُدۡرِكَ
ٱلۡقَمَرَ وَلَا ٱلَّيۡلُ سَابِقُ ٱلنَّهَارِۚ وَكُلّٞ فِي فَلَكٖ يَسۡبَحُونَ ﴿٤٠﴾

**39-40.** ጨረቃንም የመስፈሪያዎች ባለቤት ሲሆን እንደ አሮጌ ዘንባባ ቀንዘል እስኪሆን ድረስ መሄዱን ለካነው። ፀሐይ ጨረቃን ልትደርስበት አይገባትም። ሌሊትም ቀንን ያለ ጊዜው ቀዳሚ አይሆንም። ሁሉም በመዞሪያቸው (በፈለክ) ውስጥ ይዋኛሉ።

وَءَايَةٞ لَّهُمۡ أَنَّا حَمَلۡنَا ذُرِّيَّتَهُمۡ فِي ٱلۡفُلۡكِ ٱلۡمَشۡحُونِ ﴿٤١﴾ وَخَلَقۡنَا لَهُم مِّن مِّثۡلِهِۦ مَا يَرۡكَبُونَ ﴿٤٢﴾
وَإِن نَّشَأۡ نُغۡرِقۡهُمۡ فَلَا صَرِيخَ لَهُمۡ وَلَا هُمۡ يُنقَذُونَ ﴿٤٣﴾ إِلَّا رَحۡمَةٗ مِّنَّا وَمَتَٰعًا إِلَىٰ حِينٖ ﴿٤٤﴾
وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱتَّقُواْ مَا بَيۡنَ أَيۡدِيكُمۡ وَمَا خَلۡفَكُمۡ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ﴿٤٥﴾

**41-45.** እኛም የቀድሞ ትውልዳቸውን (አባቶቻቸውን) በተሞላች መርከብ ውስጥ የጫንን መሆናችን ለእነርሱ ምልክት ነው። ከመሰሉም በእርሱ የሚሳፈሩበትን ለእነርሱ ፈጠርንላቸው። ስንፈልግ እናሰምጣቸዋለን። ለእነርሱም ነፃ የሚያደርጋቸው ረዳት የላቸውም እነርሱም የሚዳኑ አይደሉም። እኛ ግን በችሮታችንና እስከ ጊዜ ሞታቸው ለማጣቀም አዳንናቸው። ለእነርሱም በስተፊታችሁና በኋላችሁ ያለውን ነገር ተጠንቀቁ ይታዘንላችኋልና በተባለ ጊዜ ፊታቸውን ያዞራሉ።

وَمَا تَأۡتِيهِم مِّنۡ ءَايَةٖ مِّنۡ ءَايَٰتِ رَبِّهِمۡ إِلَّا كَانُواْ عَنۡهَا مُعۡرِضِينَ ﴿٤٦﴾ وَإِذَا قِيلَ لَهُمۡ أَنفِقُواْ
مِمَّا رَزَقَكُمُ ٱللَّهُ قَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَنُطۡعِمُ مَن لَّوۡ يَشَآءُ ٱللَّهُ أَطۡعَمَهُۥٓ إِنۡ
أَنتُمۡ إِلَّا فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ﴿٤٧﴾ وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلۡوَعۡدُ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٤٨﴾

**46-48.** ከጌታቸው ታዕምራት አንዷት ታዕምር አትመጣላቸውም ከእርሷ የሚሸሹ ቢሆን እንጅ። ለእነርሱም አላህ ከሰጣችሁ ሲሳይ ለግሱ በተባሉ ጊዜ እነዚያ በአላህ የካዱት ለእነዚያ በአላህ ላመኑት አላህ ቢሻ ኖሮ የሚያበላውን እናበላለን? እናንተ በግልፅ ስህተት ውስጥ እንጂ በሌላ ላይ አይደላችሁም ይላሉ። እውነተኞችም እንደ ሆናችሁ ይህ ቀጠሮ መቼ ነው? ይላሉ።

ከያሲን ምዕራፍ (47) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡ በክር ሲዲቅና አቡ ጀህል ለድሆች በመስጠት ጉዳይ ተነጋግረው አቡ ጀህል ምን አገባኝ እኔ ያንተ ጌታ ቢፈልግ መስጠት ይችላል ብለሃል ከፈለገ ሊሰጣቸው ለሚችላቸው ህዝቦች ምን አገባኝና ነው እያለ ሲያፌዝ እና እንዲያውም አቡበከር ንብረትክን ለሆነ ላልሆነ ማውጣትን ግልፅ ስህተት ነው ብሎ ሲተቻቸው ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። አል -ጀዛኢሪ።

مَا يَنظُرُونَ إِلَّا صَيۡحَةٗ وَٰحِدَةٗ تَأۡخُذُهُمۡ وَهُمۡ يَخِصِّمُونَ ﴿٤٩﴾ فَلَا يَسۡتَطِيعُونَ تَوۡصِيَةٗ
وَلَآ إِلَىٰٓ أَهۡلِهِمۡ يَرۡجِعُونَ ﴿٥٠﴾ وَنُفِخَ فِي ٱلصُّورِ فَإِذَا هُم مِّنَ ٱلۡأَجۡدَاثِ إِلَىٰ رَبِّهِمۡ يَنسِلُونَ ﴿٥١﴾
قَالُواْ يَٰوَيۡلَنَا مَنۢ بَعَثَنَا مِن مَّرۡقَدِنَاۜۗ هَٰذَا مَا وَعَدَ ٱلرَّحۡمَٰنُ وَصَدَقَ ٱلۡمُرۡسَلُونَ ﴿٥٢﴾

**49-52.** እነርሱ የሚከራከሩ ሲሆኑ በድንገት የምትይዛቸው የሆነችን አንዷትን ጩኸት እንጂ ሌላን አይጠባበቁም። ያን ጊዜ መናዘዝን እንኳን አይችሉም። ወደ ቤተሰቦቻቸውም አይመለሱም። በቀንዱም ይነፋል። ወዲያውኑም እነርሱ ከየመቃብሮቻቸው ወደ ጌታቸው በፍጥነት ይገሰግሳሉ። ወይ ጥፋታችን፣ ከመኝታችን ማን ቀሰቀሰን? ይህ ያ አዛኙ ጌታ በእርሱ የቀጠረን መልዕክተኞችም እውነትን የነገሩን ነው ይላሉ።

إِن كَانَتۡ إِلَّا صَيۡحَةٗ وَٰحِدَةٗ فَإِذَا هُمۡ جَمِيعٞ لَّدَيۡنَا مُحۡضَرُونَ ﴿٥٣﴾
فَٱلۡيَوۡمَ لَا تُظۡلَمُ نَفۡسٞ شَيۡـٔٗا وَلَا تُجۡزَوۡنَ إِلَّا مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٥٤﴾

**53-54.** እርሷ አንዷት ጩኸት እንጂ ሌላ አይደለችም። ወዲያውኑም እነርሱ እኛ ዘንድ የሚሰበሰቡ የሚቀርቡ ናቸው። ዛሬም ማንኛይቱም ነፍስ ምንንም አትበደልም። ትሰሩትም የነበራችሁትን እንጂ ሌላን አትመነዱም ይባላሉ።

إِنَّ أَصۡحَٰبَ ٱلۡجَنَّةِ ٱلۡيَوۡمَ فِي شُغُلٖ فَٰكِهُونَ ﴿٥٥﴾ هُمۡ وَأَزۡوَٰجُهُمۡ فِي ظِلَٰلٍ عَلَى ٱلۡأَرَآئِكِ
مُتَّكِـُٔونَ ﴿٥٦﴾ لَهُمۡ فِيهَا فَٰكِهَةٞ وَلَهُم مَّا يَدَّعُونَ ﴿٥٧﴾ سَلَٰمٞ قَوۡلٗا مِّن رَّبّٖ رَّحِيمٖ ﴿٥٨﴾

**55-58.** የገነት ሰዎች ዛሬ በእርግጥ በስራዎች ውስጥ ተደሳቾች ናቸው። እነርሱም ሆኑ ሚስቶቻቸው በጥላዎች ውስጥ ናቸው። ባለ አጎበር አልጋዎች ላይም ተደጋፊዎች ናቸው። በውስጧ ለእነርሱ ፍራፍሬዎች አሏቸው። ለእነርሱም የሚፈልጉት ሁሉ አለላቸው። ለእነርሱም አዛኝ ከሆነው ጌታ በቃል ሰላምታ አለላቸው።

وَٱمۡتَٰزُواْ ٱلۡيَوۡمَ أَيُّهَا ٱلۡمُجۡرِمُونَ ٥٩ ۞أَلَمۡ أَعۡهَدۡ إِلَيۡكُمۡ يَٰبَنِيٓ ءَادَمَ أَن لَّا تَعۡبُدُواْ ٱلشَّيۡطَٰنَۖ
إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوّٞ مُّبِينٞ ٦٠ وَأَنِ ٱعۡبُدُونِيۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ مُّسۡتَقِيمٞ ٦١ وَلَقَدۡ أَضَلَّ مِنكُمۡ
جِبِلّٗا كَثِيرًاۖ أَفَلَمۡ تَكُونُواْ تَعۡقِلُونَ ٦٢ هَٰذِهِۦ جَهَنَّمُ ٱلَّتِي كُنتُمۡ تُوعَدُونَ ٦٣
ٱصۡلَوۡهَا ٱلۡيَوۡمَ بِمَا كُنتُمۡ تَكۡفُرُونَ ٦٤

**59-64.** ይላልም እናንተ አመፀኞች ሆይ! ዛሬ ከትክክለኛ ምእመናን ተለዩ። የአደም ልጆች ሆይ፣ ሰይጣንን አትገዙ እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና በማለት ወደ እናንተ አላዘዝኩምን? ተገዙኝም ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው (በማለትም)። ከናንተም ብዙን ፍጡር በእርግጥ አሳስቷል። የምታውቁም አልነበራችሁምን? ይህቺ ያቺ ትቀጠሩዋት የነበረችው ገሀነም ናት። ትክዱ በነበራችሁት ምክንያት ዛሬ ግቡባት ይባላሉ።

ٱلۡيَوۡمَ نَخۡتِمُ عَلَىٰٓ أَفۡوَٰهِهِمۡ وَتُكَلِّمُنَآ أَيۡدِيهِمۡ وَتَشۡهَدُ أَرۡجُلُهُم بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ٦٥ وَلَوۡ نَشَآءُ
لَطَمَسۡنَا عَلَىٰٓ أَعۡيُنِهِمۡ فَٱسۡتَبَقُواْ ٱلصِّرَٰطَ فَأَنَّىٰ يُبۡصِرُونَ ٦٦ وَلَوۡ نَشَآءُ لَمَسَخۡنَٰهُمۡ عَلَىٰ مَكَانَتِهِمۡ
فَمَا ٱسۡتَطَٰعُواْ مُضِيّٗا وَلَا يَرۡجِعُونَ ٦٧ وَمَن نُّعَمِّرۡهُ نُنَكِّسۡهُ فِي ٱلۡخَلۡقِۚ أَفَلَا يَعۡقِلُونَ ٦٨

**65-68.** ዛሬ በአፎቻቸው ላይ እናትምና እጆቻቸው ያነጋግሩናል። እግሮቻቸውም ይሰሩት በነበሩት ሁሉ ይመሰክራሉ። ብንፈልግ ኖሮ በዓይኖቻቸው ላይ በአበስን ነበር። መንገድንም እንደ ልማዳቸው በተሽቀዳደሙ ነበር። እንዴትም ያያሉ? ብንፈልግ ኖሮ በስፍራቸው ላይ እንዳሉ ወደ ሌላ ፍጥረት በለወጥናቸው ነበር። ከዚያ መሄድንም ሆነ መመለስን ባልቻሉም ነበር። እድሜውንም የምናረዝመውን ሰው በፍጥረቱ ወደ ደካማነት እንመልሰዋለን። አያውቁምን?

وَمَا عَلَّمۡنَٰهُ ٱلشِّعۡرَ وَمَا يَنۢبَغِي لَهُۥٓۚ إِنۡ هُوَ إِلَّا ذِكۡرٞ وَقُرۡءَانٞ مُّبِينٞ ٦٩
لِّيُنذِرَ مَن كَانَ حَيّٗا وَيَحِقَّ ٱلۡقَوۡلُ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ ٧٠

**69-70.** (ሙሐመድን) ቅኔንም አላስተማርነውም። ለእርሱም አይገባውም። እሱ መጽሐፉ መገሰጫና ገላጭ ቁርኣን አንጅ (ቅኔ አይደለም)። ግሳጼነቱም ልቡ ህያው የሆነን ሰው ሊያስፈራራበትና ቃሉም በከሓዲያን ላይ ይፈፀም ዘንድ ነው።

أَوَلَمْ يَرَوْا۟ أَنَّا خَلَقْنَا لَهُم مِّمَّا عَمِلَتْ أَيْدِينَآ أَنْعَـٰمًا فَهُمْ لَهَا مَـٰلِكُونَ ﴿٧١﴾ وَذَلَّلْنَـٰهَا لَهُمْ فَمِنْهَا رَكُوبُهُمْ وَمِنْهَا يَأْكُلُونَ ﴿٧٢﴾ وَلَهُمْ فِيهَا مَنَـٰفِعُ وَمَشَارِبُ ۖ أَفَلَا يَشْكُرُونَ ﴿٧٣﴾

**71-73.** እኛ እጆቻችን ከሰሩት ለእነርሱ እንስሳዎችን መፍጠራችን አያውቁምን? እነርሱም ለእሷ ባለ መብቶች ናቸው። ለእነርሱም ገራናት። ስለዚህ ከእርሷ ውስጥ የሚጋልቡት አለ። ከእሷም ይመገባሉ። ለእነርሱም በእሷ ውስጥ ሌሎች ጥቅሞችና መጠጦችም አሏቸው ታዲያ አያመሰግኑምን?

وَٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ ءَالِهَةً لَّعَلَّهُمْ يُنصَرُونَ ﴿٧٤﴾
لَا يَسْتَطِيعُونَ نَصْرَهُمْ وَهُمْ لَهُمْ جُندٌ مُّحْضَرُونَ ﴿٧٥﴾

**74-75.** መረዳትንም በመከጀል ከአላህ ሌላ አማልክትን ያዙ። ሊረዷቸው አይችሉም። እነርሱም ለእርሳቸው ወደ እሳት የተቀረቡ ሰራዊት ናቸው።

فَلَا يَحْزُنكَ قَوْلُهُمْ ۘ إِنَّا نَعْلَمُ مَا يُسِرُّونَ وَمَا يُعْلِنُونَ ﴿٧٦﴾

**76.** ንግግራቸውም አያሳዝንህ እኛ የሚደብቁትንም የሚገልፆትንም እናውቃለንና።

أَوَلَمْ يَرَ ٱلْإِنسَـٰنُ أَنَّا خَلَقْنَـٰهُ مِن نُّطْفَةٍ فَإِذَا هُوَ خَصِيمٌ مُّبِينٌ ﴿٧٧﴾ وَضَرَبَ لَنَا مَثَلًا وَنَسِىَ خَلْقَهُۥ ۖ قَالَ مَن يُحْىِ ٱلْعِظَـٰمَ وَهِىَ رَمِيمٌ ﴿٧٨﴾ قُلْ يُحْيِيهَا ٱلَّذِىٓ أَنشَأَهَآ أَوَّلَ مَرَّةٍ ۖ وَهُوَ بِكُلِّ خَلْقٍ عَلِيمٌ ﴿٧٩﴾ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُم مِّنَ ٱلشَّجَرِ ٱلْأَخْضَرِ نَارًا فَإِذَآ أَنتُم مِّنْهُ تُوقِدُونَ ﴿٨٠﴾
أَوَلَيْسَ ٱلَّذِى خَلَقَ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ بِقَـٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يَخْلُقَ مِثْلَهُم ۚ بَلَىٰ وَهُوَ ٱلْخَلَّـٰقُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٨١﴾

**77-81.** ሰውየው እኛ ከፍቶት ጠብታ የፈጠርነው መሆናችንን አላወቀምን? ወዲያውም እርሱ ትንሳኤን በመካድ ግልጽ ተከራካሪ ይሆናልን? ለእኛም ምሳሌን አደረገልን። መፈጠሩንም ረሳ። አጥንቶችን እነርሱ የበሰበሱ ሲሆኑ ህያው የሚያደርጋቸው ማነው? አለ። ያ በመጀመሪያ ጊዜ (ከኢምንት) ያስገኛት ጌታ እንደገና ህያው ያደረጋታል። እርሱም በፍጡሩ ሁሉ ሁኔታ አዋቂ ነው በለው። ያ፣ ለእናንተ ከእርጥብ ዛፍ እሳትን የፈጠረላችሁ ነው። ወዲያውኑም እናንተ ከእርሱ ታቀጣጥላላችሁ። ያ ሰማያትና ምድርን የፈጠረ ብጤያቸውን

በመፍጠር ላይ ቻይ አይደለምን? እንዴታ ቻይ ነው እንጂ። እርሱም በብዙ ፈጣሪና አዋቂ ነው።

إِنَّمَآ أَمۡرُهُۥٓ إِذَآ أَرَادَ شَيۡـًٔا أَن يَقُولَ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٨٢﴾ فَسُبۡحَٰنَ ٱلَّذِي بِيَدِهِۦ مَلَكُوتُ كُلِّ شَيۡءٖ وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ﴿٨٣﴾

**82-83.** ነገሩ አንድን ነገር በሻ ጊዜ ሁን ማለት ነው። ከዚያ ወዲያው ይሆናልም። እናም ያ የነገሩ ለሁሉ ስልጣን በእጁ የሆነው ጌታ ጥራት ይገባው። ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ።

ከያሲን ምዕራፉ ከ (77-83) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረደበት ምክንያት፡- ኡበይ ኢብኑ ኸለፍ የተባለ ሰውዬ ወደ ነብዩ (ﷺ) የበሰበሰ አጥንት ይዞ መጥቶ በእጁ እየፈረፈረ ይህንን ነው ያንተ ጌታ የሚቀሰቅሰው ሙሐመድ በማለት ሲጠይቃቸው አዎ አንተንም ከሞትክ በኋላ እንደገና ቀስቅሶ ጀሃነም ያስገባሃል። ባሉት ጊዜ ነበር እኒህ አናቅፅ የወረዱት። ዋሒዲ እና ሱዩጢ።

**ከያሲን ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-83) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህ መልዕክተኛ ነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
2. ለነብያት መላክና ቁርኣን ለመውረድ ምክንያት ምን እንደሆነ፤
3. ነብዩ (ﷺ) የተላኩበት ዘመን አንድ ነብይ ባልነበረበት ጊዜ መሆኑ፤
4. ዱንያን መውደድና በእሷ መጨነቅና አኼራን መተው የሰው ልጅ ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ እንደሚያስገባው፤
5. ወንጀሎች የሰውን ልጅ እግር በመተብተብ ከኸይር ነገር እንደሚገድበው፤
6. ለመልካም አርአያም ሆነ ወይ ለመጥፎ መንገድ የከፈተ በመጀመሪያው መንገድ የተጓዘው፤
7. የቀድርን ነገር ማረጋገጥ፤
8. ምሳሌዎችን ለትምህርት መጥቀስ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
9. ሁልጊዜም የከሓዲያን ባህሪ ተመሳሳይ ስለመሆኑ፤
10. ከሓዲያን ማስረጃን መቃወም ሲያቅታቸው ኃይል እንደሚያዘነብሉ፤
11. በኢስላም በመጥፎ ገድ ማመን እንደሌለ፤
12. ያ በቁሙም ሆነ ሙቶ ህዝቦቹን የመከረው ሰውዬ ትልቅነት፤
13. የተውሒድ አስተማሪዎች በየጊዜው የሚያጋጥማቸው ችግር፤
14. እውነትን ማሳወቅና ማድረስ አስፈላጊው መስዋዕት ከፍሎ ማድረግ ግዴታ ስለመሆኑ፤
15. ሙዕሚን በተለይም ለዲን ሲሰዋ ሲሞት እንደሚበሰር እንማራለን፤
16. የአንጧኪያን ሰዎች በማጥፋት የአላህን ኃይል ማሳየቱ፤
17. ፍጡሮች በራሳቸው ፀፀታቸው ይፋ ማውጣ፤
18. በአላህ ህግጋቶች በሆነው በአንዱም ማፌዝ ክልክል ስለ መሆኑ፤
19. ካለፉት ሰዎች ህይወት ታሪክ መማር እንዳለብን፤
20. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
21. ሙቶ መነሳትን አምኖ መቀበል፤
22. አብዛሀኛው ፍጡር ጥንድ አድርጎ መፍጠሩ ቁርኣን መናገሩ የአሏህ ቃል ለመሆኑ ትልቅ ማስረጃ እንደሆነ፤

23. አላህን በማመንና እሱን በመታዘዝ ማመስገን ግዴታ ስለ መሆኑ፤
24. አብዛሀኛው ፍጡር ጥንድ አድርጎ መፍጠሩ ቁርኣን መናገሩ አላህ ቃል ለመሆኑ ትልቅ ማስረጃ እንደሆነ፤
25. አላህን በማመንና እሱን በመታዘዝ ማስመስገን ግዴታ ስለ መሆኑ፤
26. ሙቶ መነሳት ሀቅ ስለመሆኑ ግልፅ ማስረጃዎች ማቅረብ፤
27. የስነ ፈለክን ጉዳይ ቁርኣን ማውሳቱ ቁርኣን ከአላህ የመጣ ለመሆኑ ብቸኛ ማስረጃ እንደሆነ፤
28. አላህ በኑህ ሰዎች መካከል ዘሮችን በማስቀረቱ ለሰዎች የዋለው ውለታ፤
29. አላህ ለባሮቹ የዋለው ውለታና ጥበቃ እንዲሁም እንክብካቤ፤
30. የቁረይሾች ሞገድ ቢጤ ያልነበረው እንደነበር፤
31. መርከብ ብዙ አይነት ጥቅሞች እንዳለው መጠቆሙ፤
32. ከሓዲያን ያለባቸው ትዕቢትና ሞገድን መግለፅ፤
33. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
34. ትንሳኤ በድንገት እንጂ እንደማትመጣ፤
35. ዓለምን የሚያፈራርሰው መልአክ የሚነፋው ስንት ጊዜ እንደሆነ የዐሊሞች ልዩነት ቢኖረውም ተቀባይነት ያለው ሦስት ጊዜ የሚለው ነው እሱም፡-
    1. ማጥፊያ፤
    2. ማስባተቻና ማስደንገጫ፤
    3. መቀስቀሻ።
36. የአላህን ፍትሀዊነት፤
37. ከሞቱ በኋላ መመለስን ማፅደቅ፤
38. የጀነትን ፀጋዎች ማውሳት፤
39. አማኞች በጀነት የአላህን ሰላምታ እንደሚያገኙ፤
40. ከሞት በኋላ መነሳትን ማረጋገጥ፤
41. ሰይጣን ለሰው ልጅ ያለውን ጠላትነት ማጠንከር፤
42. ሰዎች የትንሳኤን ዕለት ምንም ነገር መደበቅ እንደማይችሉ፤
43. አላህ ሰዎችን ወደ እንስሳ በመቀየር ሊቀጣ እንደሚችል ማስጠንቀቅ፤
44. የሰው ልጅ ከኃይል በኋላ ወደ ደካማነት በመመለስ የአላህን ኃያልነት ማሳየት
45. የነብዩ የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ነብይነት ቁርኣን ከሓዲያን እንደመሉት ዘፈን ሳይሆን ማስታወሺያና መገሰፃ መሆኑን፤
46. ለቁርኣን መውረድ ዋናው ምክንያት ምን እንደሆነ፤
47. ቁርኣንን በሕይት ላሉ ሰዎች ማንበብ ሲገባቸው ለሞቱ የሚያነቡ ሰዎች ምን ያህል ስህተት ላይ እንደሆኑ፤
48. የአላህን ፀጋ እያስታወሱ ማመስገን ተገቢ መሆኑን፤
49. ጣኦት አምላኪዎች የነበረባቸው ሞኝነት ምን እንደነበር፤
50. ለሙቶ መነሳት ሀቅነት አራት ማስረጃዎችን ማቅረብ ማረጋገጥ፤
51. በክርክር ጊዜ አዕምሮ መጠቀም ተገቢ ስለመሆኑ፤
52. አላህ ከደካማነት፤ ከጉድለት፤ ከረዳት፤ ከልጅና ከሚስት ማጥራት፤
53. ሁሉ ነገር በአላህ እጅና ቁጥጥር ስር መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የያሲን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (37)
# የተሰላፊዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አስሷፋት)

سُورَةُ الصَّافَّاتِ

**በመካ ነው የወረደው። የአናቅፅ ብዛት (182) ናቸው።**

**የሱረቱ አስ-ሷፋት መግቢያ**

*መካዊ እንደመሆኑ ሁሉ ሶስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ማለትም በአላህ አንድነት፣ በሙቶ መነሳት ሐቅነትና ስለ ወህይ ያስተምራል። ሲጀምር ስለመላይኮች ከዚያ ስለ ጂኖችና ስለ ሙቶ መነሳት በማብራራት ነው። በአንድ አማኝና በአንድ ከሃዲ መካከል የተካሄዱን ውይይትም በማውሳት የእምነትን አስፈላጊነት አስምሮበታል። ከነብዩ ኑህ አንስቶ የአያሌ ነብያትን ታሪክ ዘርዝሯል። በተለይም አባትና ልጅ የሆኑት ኢብራሂምና ኢስማኢል የደረሰባቸዉን ፈተና በሰፊው ይተነትናል። በስተመጨረሻም በሁለቱም አለም ድል የኋላኋላ ምእመናን እንደሚሆን በማብሰር መልዕክቱን ይደመድማል።*

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَٱلصَّٰٓفَّٰتِ صَفّٗا ١ فَٱلزَّٰجِرَٰتِ زَجۡرٗا ٢ فَٱلتَّٰلِيَٰتِ ذِكۡرًا ٣ إِنَّ إِلَٰهَكُمۡ لَوَٰحِدٞ ٤
رَّبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا وَرَبُّ ٱلۡمَشَٰرِقِ ٥

**1-5.** መሰለፍን የሚሰለፉት፣ መገሰፅን የሚገሰፁት ቁርአንንም በሚያነቡት እምላለሁ። አምላካችሁ በእርግጥ አንድ ብቻ ነው። እርሱ በሰማያትና በምድር በመካካለቸው ያለውን ፍጡር ሁሉ ጌታ ነው። የምስራቆችም ጌታ ነው።

إِنَّا زَيَّنَّا ٱلسَّمَآءَ ٱلدُّنۡيَا بِزِينَةٍ ٱلۡكَوَاكِبِ ٦ وَحِفۡظٗا مِّن كُلِّ شَيۡطَٰنٖ مَّارِدٖ ٧
لَّا يَسَّمَّعُونَ إِلَى ٱلۡمَلَإِ ٱلۡأَعۡلَىٰ وَيُقۡذَفُونَ مِن كُلِّ جَانِبٖ ٨ دُحُورٗاۖ وَلَهُمۡ عَذَابٞ
وَاصِبٌ ٩ إِلَّا مَنۡ خَطِفَ ٱلۡخَطۡفَةَ فَأَتۡبَعَهُۥ شِهَابٞ ثَاقِبٞ ١٠

**6-10.** ቅርቢቱን ሰማይ በከዋክብት ጌጥ አጌጥናት (አስዋብናት)። አመፀኛ ከሆነ ሰይጣን ሁሉ መጠበቅን ጠበቅናት። ወደ ላይኛው ሰራዊት አያደምጡም፤ ከእያአቅጣጫው ሁሉ ችቦ ይጣልባቸዋል፣ (ይቀጠቀጣሉ)። የሚባረሩ ሲሆኑ (ይጣልባቸዋል)፤ ለእነርሱም ዘወታሪ ቅጣት አለባቸው። ንጥቂያን የነጠቀ ወዲያውኑ አብሪ ኮከብ የተከተለው ሲቀር (እርሱ ይሰማዋል)።

فَٱسۡتَفۡتِهِمۡ أَهُمۡ أَشَدُّ خَلۡقًا أَم مَّنۡ خَلَقۡنَآۚ إِنَّا خَلَقۡنَٰهُم مِّن طِينٖ لَّازِبِۭ ﴿١١﴾
بَلۡ عَجِبۡتَ وَيَسۡخَرُونَ ﴿١٢﴾ وَإِذَا ذُكِّرُواْ لَا يَذۡكُرُونَ ﴿١٣﴾ وَإِذَا رَأَوۡاْ ءَايَةٗ يَسۡتَسۡخِرُونَ ﴿١٤﴾
وَقَالُوٓاْ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا سِحۡرٞ مُّبِينٌ ﴿١٥﴾ أَءِذَا مِتۡنَا وَكُنَّا تُرَابٗا وَعِظَٰمًا أَءِنَّا لَمَبۡعُوثُونَ ﴿١٦﴾
أَوَ ءَابَآؤُنَا ٱلۡأَوَّلُونَ ﴿١٧﴾

**11-17.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዚያ ጠይቃቸው፤ እነርሱ በአፈጣጠር ይበልጥ የበረቱ ናቸውን? ወይስ እኛ ከእነርሱ በፊት የፈጠረነው ፍጡር? እኛ ከሚጣበቅ ጭቃ ፈጠርናቸው። ይልቁንም ማስተባበላቸው አስደነቀህ በመደነቅህ ይሳለቃሉ። በተገሰፁም ጊዜ አይገሰፁም። ታዐምርን ባዩ ጊዜ ለመሳለቅ ይጣጣራሉ። ይህ ግልፅ ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም። በሞትንና ዐፈርና አጥንቶችም በሆነ ጊዜ የምንቀስቀስ ነን? የቀድሞዎቹ አባቶቻችንም እንደዚሁ ይቀሰቀሳሉ ይላሉ።

قُلۡ نَعَمۡ وَأَنتُمۡ دَٰخِرُونَ ﴿١٨﴾

**18.** አዎን እናንተ ወራዶች ሆናችሁ (ትነሳላችሁ) በላቸው።

فَإِنَّمَا هِيَ زَجۡرَةٞ وَٰحِدَةٞ فَإِذَا هُمۡ يَنظُرُونَ ﴿١٩﴾ وَقَالُواْ يَٰوَيۡلَنَا هَٰذَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ﴿٢٠﴾
هَٰذَا يَوۡمُ ٱلۡفَصۡلِ ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ﴿٢١﴾

**19-21.** «እርሷም አንዲት ጩኸት ብቻ ናት። እነርሱም ወዲያውኑ ምን እንደሚፈፀምባቸው ያያሉ። ዋ፣ ጥፋታችን፣ ይህ የፍርዱ ቀን ነው ይላሉም። ይህ ያ በእርሱ ታስተባብሉት የነበራችት መለያው ቀን ነው ይላሉ።

**ከተሰላፊዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-21) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ከፍጡሮቹ በፈለገው መማል እንደሚችል፤
2. ተውሒድን ማፅደቅ፤
3. በሰማይ ኮከብ የመገኘቱ ምክንያት፤
4. ሰይጣን ወደ ሰማይ መድረስ አለመቻሉ፤

۞ٱحۡشُرُواْ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ وَأَزۡوَٰجَهُمۡ وَمَا كَانُواْ يَعۡبُدُونَ ﴿٢٢﴾ مِن دُونِ ٱللَّهِ فَٱهۡدُوهُمۡ إِلَىٰ
صِرَٰطِ ٱلۡجَحِيمِ ﴿٢٣﴾ وَقِفُوهُمۡۖ إِنَّهُم مَّسۡـُٔولُونَ ﴿٢٤﴾ مَا لَكُمۡ لَا تَنَاصَرُونَ ﴿٢٥﴾ بَلۡ هُمُ ٱلۡيَوۡمَ
مُسۡتَسۡلِمُونَ ﴿٢٦﴾ وَأَقۡبَلَ بَعۡضُهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٖ يَتَسَآءَلُونَ ﴿٢٧﴾

**22-27.** (ለመላዕክቶችም) እነዚያ ነፍሶቻቸውን የበደሉትን፣ ሰዎች ጓደኞቻቸውንም ከአላህ ሌላ ይገዟቸው የነበሩትንም ጣዖታትን በአንድ ሰብስቡ። ከአላህ ሌላ (የሚገዟቸውን ሰብስቧቸው) ከዚያ ወደ ገሀነም መንገድም ምሯቸው። እነርሱ ተጠያቂዎች ናቸውና አቁሟቸውም (ይባላል)። ለነርሱም ምን ሆናችሁ ነው የማትረዳዱት ይባላሉ። በእርግጥ እነርሱ ዛሬ እጃቸውን ለአላህ የሰጡ ማምለጫ የሌላቸው ወራዳዎች ናቸው። እርስ በራሳቸው የሚወቃቀሱም ሆነው ይመጣሉ።

قَالُوٓاْ إِنَّكُمۡ كُنتُمۡ تَأۡتُونَنَا عَنِ ٱلۡيَمِينِ ﴿٢٨﴾ قَالُواْ بَل لَّمۡ تَكُونُواْ مُؤۡمِنِينَ ﴿٢٩﴾ وَمَا كَانَ لَنَا عَلَيۡكُم مِّن سُلۡطَٰنِۭۖ بَلۡ كُنتُمۡ قَوۡمٗا طَٰغِينَ ﴿٣٠﴾ فَحَقَّ عَلَيۡنَا قَوۡلُ رَبِّنَآۖ إِنَّا لَذَآئِقُونَ ﴿٣١﴾ فَأَغۡوَيۡنَٰكُمۡ إِنَّا كُنَّا غَٰوِينَ ﴿٣٢﴾

**28-32.** ተከታዩች ለአስከታዩቻቸው እናንተ በጉልበት ትመጡብን ነበር ይላሉ። አስከታዩቹም ይላሉ:- አይደለም ፈፅሞ ምዕመናን አልነበራችሁም። ለእኛም በናንተ ላይ ምንም ስልጣን አልነበረንም። በእርግጥ እናንተ ጠማሞች ህዝቦች ነበራችሁና ነው እንጂ። በእኛም ላይ የጌታችን ቃል የተረጋገጠብንና ሁላችንም ቅጣትን ቀማሽ ነን። እኛ ጠማሞች ስለ ነበርን ወደ ጥመት ጠራናችሁም ይላሉ።

فَإِنَّهُمۡ يَوۡمَئِذٖ فِي ٱلۡعَذَابِ مُشۡتَرِكُونَ ﴿٣٣﴾ إِنَّا كَذَٰلِكَ نَفۡعَلُ بِٱلۡمُجۡرِمِينَ ﴿٣٤﴾ إِنَّهُمۡ كَانُوٓاْ إِذَا قِيلَ لَهُمۡ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ يَسۡتَكۡبِرُونَ ﴿٣٥﴾ وَيَقُولُونَ أَئِنَّا لَتَارِكُوٓاْ ءَالِهَتِنَا لِشَاعِرٖ مَّجۡنُونِۭ ﴿٣٦﴾

**33-36.** ስለዚህ እነርሱ በዚያ ቀን በቅጣቱ ተጋሪዎች ናቸው። እኛ በአመፀኞች ሁሉ እንደዚህ እንሰራለን። እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም። በተባለ ጊዜ ይኮሩ ነበሩ። እኛ ለዕብድ ባለቅኔ ብለን አማልክቶቻችንን የምንተው ነን? ይሉ ነበር።

بَلۡ جَآءَ بِٱلۡحَقِّ وَصَدَّقَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿٣٧﴾ إِنَّكُمۡ لَذَآئِقُواْ ٱلۡعَذَابِ ٱلۡأَلِيمِ ﴿٣٨﴾ وَمَا تُجۡزَوۡنَ إِلَّا مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٣٩﴾ إِلَّا عِبَادَ ٱللَّهِ ٱلۡمُخۡلَصِينَ ﴿٤٠﴾ أُوْلَٰٓئِكَ لَهُمۡ رِزۡقٞ مَّعۡلُومٞ ﴿٤١﴾ فَوَٰكِهُ وَهُم مُّكۡرَمُونَ ﴿٤٢﴾ فِي جَنَّٰتِ ٱلنَّعِيمِ ﴿٤٣﴾ عَلَىٰ سُرُرٖ مُّتَقَٰبِلِينَ ﴿٤٤﴾ يُطَافُ عَلَيۡهِم بِكَأۡسٖ مِّن مَّعِينِۭ ﴿٤٥﴾ بَيۡضَآءَ لَذَّةٖ لِّلشَّٰرِبِينَ ﴿٤٦﴾ لَا فِيهَا غَوۡلٞ وَلَا هُمۡ عَنۡهَا يُنزَفُونَ ﴿٤٧﴾ وَعِندَهُمۡ قَٰصِرَٰتُ ٱلطَّرۡفِ عِينٞ ﴿٤٨﴾ كَأَنَّهُنَّ بَيۡضٞ مَّكۡنُونٞ ﴿٤٩﴾

**37-49.** አይደለም እውነቱን ሃይማኖት አመጣ፤ መልዕክተኞችም እውነተኝነታቸውን አረጋገጠ። እናንተ አሳማሚውን ቅጣት በእርግጥ ቀማሾች ናችሁ። ትሰሩትም የነበራችሁትን እንጂ ሌላን አትመነዱም። ግን ምርጥ የሆኑት የአላህ ባሮች ቅጣትን አይቀምሱም። እነዚያ ለእነርሱ የታወቀ ሲሳይ አለላቸው። ፍራፍሬዎች (አሉላቸው) እነርሱም የተከበሩ ናቸው። በድሎት ገነቶች ውስጥ። ፊት ለፊት የሚታያዩ ሲሆን በአልጋዎች ላይ (ይንፈላሰሳሉ)። ከሚመነጭ ወይን ጠጅ በያዙ ብርጭቆ በእነርሱ ላይ ይዞርባቸዋል። ነጭ ለጠጪዎች ጣፋጭ ከሆነች፤ በእርሷ ውስጥም ምታት የለባትም። እነርሱ ከእርሷ የሚሰክሩ አይደሉም። እነርሱ ዘንድ ዓይናቸውን በባሎቻቸው ላይ አሳጣሪዎች የሆኑ ዓይናማ ሴቶች አሉ። እነርሱ ልክ የተሸፈነ (የሰጎን) እንቁላል ይመስላሉ።

فَأَقْبَلَ بَعْضُهُمْ عَلَىٰ بَعْضٍ يَتَسَآءَلُونَ ﴿٥٠﴾ قَالَ قَآئِلٌ مِّنْهُمْ إِنِّي كَانَ لِي قَرِينٌ ﴿٥١﴾ يَقُولُ
أَءِنَّكَ لَمِنَ ٱلْمُصَدِّقِينَ ﴿٥٢﴾ أَءِذَا مِتْنَا وَكُنَّا تُرَابًا وَعِظَٰمًا أَءِنَّا لَمَدِينُونَ ﴿٥٣﴾ قَالَ هَلْ أَنتُم
مُّطَّلِعُونَ ﴿٥٤﴾ فَٱطَّلَعَ فَرَءَاهُ فِي سَوَآءِ ٱلْجَحِيمِ ﴿٥٥﴾ قَالَ تَٱللَّهِ إِن كِدتَّ لَتُرْدِينِ ﴿٥٦﴾ وَلَوْلَا
نِعْمَةُ رَبِّي لَكُنتُ مِنَ ٱلْمُحْضَرِينَ ﴿٥٧﴾

**50-57.** የሚጠያየቁም ሆነው ከፊላቸው ወደ ከፊሉ ይመጣሉ። ከእነርሱ የሆነ ተናጋሪ እኔ ጓደኛ ነበረኝ ይላል። እርግጥ አንተ ከሚያምኑት ነህን? የሚል በሞትንና ዐፈር አጥንቶችም በሆነ ጊዜ እኛ በእርግጥ እኛ እንመረመራለን? የሚል። እናንተ ተመልካቾች ናችሁን? ይላል። ይመለከታልም በገሀነም መካከልም ጓደኛውን ያየዋል። ይላል በአላህ እምላለሁ በእርግጥ ልታጠፋኝ ቀርበህ ነበር። የጌታየም ፀጋ ባልነበረ ኖሮ ወደ እሳት ከሚቀርቡት እሆን ነበር።

أَفَمَا نَحْنُ بِمَيِّتِينَ ﴿٥٨﴾ إِلَّا مَوْتَتَنَا ٱلْأُولَىٰ وَمَا نَحْنُ بِمُعَذَّبِينَ ﴿٥٩﴾ إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ ٱلْفَوْزُ
ٱلْعَظِيمُ ﴿٦٠﴾ لِمِثْلِ هَٰذَا فَلْيَعْمَلِ ٱلْعَٰمِلُونَ ﴿٦١﴾

**58-61.** የገነት ሰዎች ይላሉ እኛ የምንሞትም አይደለንም? የመጀመሪያይቱ መሞታችን ብቻ ስትቀር እኛም የምንቀጣ አይደለንምን? ይላሉ። ይህ ለገነት ሰዎች የተወሳው እርሱ በእርግጥ ታላቅ እድል ነው። ለዚህ ብጤ ሰሪዎች ይስሩ።

أَذَٰلِكَ خَيۡرٞ نُّزُلًا أَمۡ شَجَرَةُ ٱلزَّقُّومِ ﴿٦٢﴾ إِنَّا جَعَلۡنَٰهَا فِتۡنَةٗ لِّلظَّٰلِمِينَ ﴿٦٣﴾
إِنَّهَا شَجَرَةٞ تَخۡرُجُ فِيٓ أَصۡلِ ٱلۡجَحِيمِ ﴿٦٤﴾ طَلۡعُهَا كَأَنَّهُۥ رُءُوسُ ٱلشَّيَٰطِينِ ﴿٦٥﴾
فَإِنَّهُمۡ لَأٓكِلُونَ مِنۡهَا فَمَالِـُٔونَ مِنۡهَا ٱلۡبُطُونَ ﴿٦٦﴾ ثُمَّ إِنَّ لَهُمۡ عَلَيۡهَا لَشَوۡبٗا مِّنۡ حَمِيمٖ ﴿٦٧﴾
ثُمَّ إِنَّ مَرۡجِعَهُمۡ لَإِلَى ٱلۡجَحِيمِ ﴿٦٨﴾

**62-68.** በመስተንግዶነት ይህ ይበልጣልን? ወይስ የዘቁም ዛፍ? እኛ ለበዳዩች ፈተና አድርገናታል። እርሷ በገሀነም አዘቅት ውስጥ የምትወጣ ዛፍ ናት፤ እንቡጧ ልክ የሰይጣናት ራሶች ይመስላል። እነርሱ ከእርሷ በይዎች ናቸው። ሆዶችንም ከእርሷ ሞይዎች ናቸው። ከዚያ ለእነርሱ ከእርሷ ላይ ከተኳሳ ውሃ ቅልቅልን መጠጥ አላቸው። ከዚያ መመለሻቸው ወደ ተጋጋመች እሳት ነው።

ከተሰላፊዎች (66-68) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አቡጀህል ይህ ሰውያችሁ በእሳት ውስጥ ዛፍ አለ ብሎ ይናገራል እሳት ደግሞ ዛፍን ትበላለች እንጂ አታበቅልም በማለት ሲያፌዝ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ።)

إِنَّهُمۡ أَلۡفَوۡاْ ءَابَآءَهُمۡ ضَآلِّينَ ﴿٦٩﴾ فَهُمۡ عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِمۡ يُهۡرَعُونَ ﴿٧٠﴾ وَلَقَدۡ ضَلَّ قَبۡلَهُمۡ أَكۡثَرُ
ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٧١﴾ وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا فِيهِم مُّنذِرِينَ ﴿٧٢﴾ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُنذَرِينَ ﴿٧٣﴾
إِلَّا عِبَادَ ٱللَّهِ ٱلۡمُخۡلَصِينَ ﴿٧٤﴾

**69-74.** እነርሱ አባቶቻቸውን የተሳሳቱ ሆነው አግኝተዋል። እነርሱም በፍላጎታቸው ላይ ይገሰግሳሉ። ከእነርሱም በፊት የነበሩት የቀድሞዎቹ ህዝቦች አብዛሀኞቻቸው በእርግጥ ተሳስተዋል። በውስጣቸውም አስፈራሪዎችን በእርግጥ ልከናል። የተስፈራሪዎቹም መጨረሻ እንዴት እንደነበረ ተመልከት። ምርጥ የሆኑት የአላህ ባሮች ብቻ ሲቀሩ።

وَلَقَدۡ نَادَىٰنَا نُوحٞ فَلَنِعۡمَ ٱلۡمُجِيبُونَ ﴿٧٥﴾ وَنَجَّيۡنَٰهُ وَأَهۡلَهُۥ مِنَ ٱلۡكَرۡبِ ٱلۡعَظِيمِ ﴿٧٦﴾
وَجَعَلۡنَا ذُرِّيَّتَهُۥ هُمُ ٱلۡبَاقِينَ ﴿٧٧﴾ وَتَرَكۡنَا عَلَيۡهِ فِي ٱلۡأٓخِرِينَ ﴿٧٨﴾ سَلَٰمٌ عَلَىٰ نُوحٖ فِي
ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٧٩﴾ إِنَّا كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٨٠﴾ إِنَّهُۥ مِنۡ عِبَادِنَا ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٨١﴾
ثُمَّ أَغۡرَقۡنَا ٱلۡأٓخَرِينَ ﴿٨٢﴾

**75-82.** ኑህም በእርግጥ ጠራን ጥሪውን ተቀባዩቹ ምርጥ የሆኑት የአላህ ባሮች ብቻ ሲቀሩ። ምንኛ አማርን? እርሱም ቤተሰቦቹንም ከከባድ ጭንቅ አዳንን። ዘሮቹንም እነርሱን ብቻ ቀሪዎች አደረግን። በእርሱም ላይ በኋለኞቹ ህዝቦች ውስጥ መልካምን ዝና ተውን። በዓለማት ውስጥ ሰላም በኑህ ላይ ይሁን። እኛ እንደዚሁ መልካም ሰሪዎች እንመነዳለን። እርሱ ከምዕመናን ባሮቻችን ነውና። ከዚያ ሌሎችን አሰመጥን።

**ከተሰላፊዎች ምዕራፉ ከአንቀፅ (22-82) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቂያማ ቀን ኬላዎች አንዱን ማስታወስ፤
2. በክህደትና በወንጀል የተመሳሰሉ ሰዎች በአንድ እንደሚቀሰቀሱ፤
3. አምላኪዎች ከተመላኪዎች ነፃ መሆናቸው ፋይዳ እንደሌለው
4. የተሳሳተ ሁሉ ጥፉ እንደሆነ፤
5. መኮች ለነብዩ (ﷺ) ይሏቸው የነበሩትን አሉባልታና ውሸት ማጋለጥ፤
6. ላኢላሀኢለሏህ የነብያት ሁሉ ጥሪ እንደነበረች፤
7. ተውሒድንና ሙቶ መነሳትን ማረጋጥ
8. በክህደትና በወንጀል የተመሳሰሉ ሰዎች በአንድ እንደሚቀሰቁሱ፤
9. አምላኪዎች ከተመላኪዎች ነፃ መሆናቸው ፋይዳ እንደሌለው
10. የተሳሳተ ሁሉ ጥፉ እንደሆነ፤
11. መኮች»የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ይሏቸው የነበሩትን አሉባልታና ውሸት፤
12. የአላህን ፍትሀዊነት ማሳየት፤
13. የአላህን ችሮታ በግልፅ ማስታወስ፤
14. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት በግልፅ ማስተማር፤
15. የጀነትን ምግቦች መጠጦች በአጠቃላይ ኑሮ ምን እንደሚመስል
16. አማኞችን በገሀነም ውስጥ ያሉትን ሰዎች በግልፅ በማሳየት ያሳየው ኃያልነት፤
17. ከመጥፎ ጓደኛ ራስን መጠበቅ፤
18. ከሓዲያን በሙዕሚኖች ላይ ያደረጉት የነበረው ፌዝ ምን እንደሚመስል፤
19. በሁለተኛው ዓለም ሞት እንደሌለ፤
20. መልካም ስራን ማብዛትና ከመጥፎ ተግባር መራቅ እንዳለብን
21. ከዳዕዋ ዘዴዎች መካከል ተመራጭ ማስፈራራትና ማብሰር በአንድ አድርጎ ማቅረብ ስለመሆኑ
22. ሙቶ መነሳት ሀቅ መሆኑን ማረጋገጥ፤
23. በስህተት አባትንና አያትን መንገድ መከተል፤
24. አላህ ግፈኞችን አጥፍቶ አማኞችን ነፃ ማውጣቱን
25. አላህ ወዳጆችም አክብሮ ጠላቶቹን እንደሚዋርድ፤
26. አላህ ለሷሊሆችን ዱዓ በተለይም የተበደሉ ጊዜ እንደሚቀበላቸው፤
27. መልካምን ስራ መጨረሻውም የሚያምር እንደሆነ፤
28. እምነት ለአኼራም ሆነ ለዱንያ ያለውን ከፍተኛ ጥቅም እንማራለን።

۞ وَإِنَّ مِن شِيعَتِهِۦ لَإِبۡرَٰهِيمَ ٨٣ إِذۡ جَآءَ رَبَّهُۥ بِقَلۡبٖ سَلِيمٍ ٨٤ إِذۡ قَالَ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦ
مَاذَا تَعۡبُدُونَ ٨٥ أَئِفۡكًا ءَالِهَةٗ دُونَ ٱللَّهِ تُرِيدُونَ ٨٦ فَمَا ظَنُّكُم بِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٨٧
فَنَظَرَ نَظۡرَةٗ فِي ٱلنُّجُومِ ٨٨ فَقَالَ إِنِّي سَقِيمٞ ٨٩ فَتَوَلَّوۡاْ عَنۡهُ مُدۡبِرِينَ ٩٠ فَرَاغَ
إِلَىٰٓ ءَالِهَتِهِمۡ فَقَالَ أَلَا تَأۡكُلُونَ ٩١ مَا لَكُمۡ لَا تَنطِقُونَ ٩٢ فَرَاغَ عَلَيۡهِمۡ ضَرۡبَۢا
بِٱلۡيَمِينِ ٩٣ فَأَقۡبَلُوٓاْ إِلَيۡهِ يَزِفُّونَ ٩٤ قَالَ أَتَعۡبُدُونَ مَا تَنۡحِتُونَ ٩٥ وَٱللَّهُ خَلَقَكُمۡ وَمَا
تَعۡمَلُونَ ٩٦ قَالُواْ ٱبۡنُواْ لَهُۥ بُنۡيَٰنٗا فَأَلۡقُوهُ فِي ٱلۡجَحِيمِ ٩٧ فَأَرَادُواْ بِهِۦ كَيۡدٗا فَجَعَلۡنَٰهُمُ
ٱلۡأَسۡفَلِينَ ٩٨ وَقَالَ إِنِّي ذَاهِبٌ إِلَىٰ رَبِّي سَيَهۡدِينِ ٩٩ رَبِّ هَبۡ لِي مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ١٠٠
فَبَشَّرۡنَٰهُ بِغُلَٰمٍ حَلِيمٖ ١٠١ فَلَمَّا بَلَغَ مَعَهُ ٱلسَّعۡيَ قَالَ يَٰبُنَيَّ إِنِّيٓ أَرَىٰ فِي ٱلۡمَنَامِ أَنِّيٓ أَذۡبَحُكَ
فَٱنظُرۡ مَاذَا تَرَىٰۚ قَالَ يَٰٓأَبَتِ ٱفۡعَلۡ مَا تُؤۡمَرُۖ سَتَجِدُنِيٓ إِن شَآءَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلصَّٰبِرِينَ ١٠٢
فَلَمَّآ أَسۡلَمَا وَتَلَّهُۥ لِلۡجَبِينِ ١٠٣ وَنَٰدَيۡنَٰهُ أَن يَٰٓإِبۡرَٰهِيمُ ١٠٤ قَدۡ صَدَّقۡتَ ٱلرُّءۡيَآۚ إِنَّا كَذَٰلِكَ
نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١٠٥ إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ ٱلۡبَلَٰٓؤُاْ ٱلۡمُبِينُ ١٠٦ وَفَدَيۡنَٰهُ بِذِبۡحٍ عَظِيمٖ ١٠٧ وَتَرَكۡنَا
عَلَيۡهِ فِي ٱلۡأٓخِرِينَ ١٠٨ سَلَٰمٌ عَلَىٰٓ إِبۡرَٰهِيمَ ١٠٩ كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ١١٠ إِنَّهُۥ مِنۡ
عِبَادِنَا ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١١١ وَبَشَّرۡنَٰهُ بِإِسۡحَٰقَ نَبِيّٗا مِّنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ١١٢ وَبَٰرَكۡنَا عَلَيۡهِ وَعَلَىٰٓ
إِسۡحَٰقَۚ وَمِن ذُرِّيَّتِهِمَا مُحۡسِنٞ وَظَالِمٞ لِّنَفۡسِهِۦ مُبِينٞ ١١٣

**83-113.** (ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂም በእርግጥ ከኑህ ተከታዩች አንዱ ነው። ወደ ጌታህ በቅን ልብ በመጣ ጊዜ (የሆነውን አስታውስ)። ለአባቱና ለህዝቦቹ ምንን ትገዛላችሁ ባለ ጊዜ ለቅጥፈት ብላችሁ ከአላህ ሌላ አማልክትን ትሻላችሁን? በዓለማት ጌታ ሀሳባችሁ ምንድ ነው?። በከዋክብት ዙሪያ መመልከትን ተመለከተ። እኔ በሽተኛ ነኝም አለ። እነርሱ ከእርሱም የሸሹ ሆነው ሄዱ። ከዚያ እሱ ወደ አማልዕክቶቻቸው ተዘነበለ፤ አለም፦ አትበሉም እንዴ ምንም የማትናገበትሩ ምን ምክኒያት አላችሁ? በኃይል የሚመታቸውም ሆኖ በእነርሱ ላይ በድብቅ ተዘነበለ። ወደ እርሱም ሰዎች እየሮጡ መጡ። የምትጠርቡትን ትገዛላችሁን? አላህ እናንተንም ሆነ የምትሰሩትን ሁሉ የፈጠረ ሲሆን በላቸው። ለእርሱም ግንብን ገንቡ በእሳት ነበልባል ውስጥ ጣሉትም አሉ። ለእርሱ ተንኮልን አሰቡ ዝቅተኞችም አደረግናቸው። አለም፦ እኔ ወደ ጌታዩ ሂጅ ነኝ፤ በእርግጥ ይመራኛልና። ጌታዩ ሆይ! ከመልካሞቹ የሆነን ልጅ

ሰጠኝ። ታጋሽም በሆነ ወጣት ልጅም አበሰርነው። ከእርሱ ጋርም (ለስራ) በደረሰ ጊዜ ልጄ ሆይ! እኔ በህልሜ እኔ የማርድህ ሆኜ አያለሁ ተመልከትም ምን ታያለህ? አለው አባቴ ሆይ! የታዘዝከውን ስራ፤ አላህ ቢሻ ከታጋሾች ሆኜ ታገኘኛለህ አለ። ሁለቱም ትዕዛዙን በተቀበሉና በግንባሩም ጎን ላይ በጣለው ጊዜ (የሆነው ሆነ)። ጠራነውም አልነው ኢብራሂም ሆይ! ራዕዩን በእውነት አረጋገጥክ። እኛ እንደዚሁ መልካም ሰሪዎችን እንመነዳለን። ይህ እርሱ በእውነት ግልፅ ፈተና ነው። በታላቅ እርድም መስዕዋት ተበዠ ነው። በእርሱም ላይ በኋለኞች ህዝቦች ውስጥ መልካምን ዝናን አስቀረንለት። ሰላም በኢብራሂም ላይ ይሁን። እንደዚሁም መልካም ሰሪዎችን ሁሉ እንመነዳለን። እርሱ በእርግጥ ካመኑት ባሮቻችን ነው። በኢስሐቅም አበሰርነው ከመልካሞች የሆነ ነብይ ሲሆን። በእርሱና በኢስሐቅ ሰላም ባረክን ከሁለቱም ዘሮች በጎ ሰሪ አለ። ለነፍሱም ግልፅ በዳይ አለ።

وَلَقَدْ مَنَنَّا عَلَىٰ مُوسَىٰ وَهَٰرُونَ ﴿١١٤﴾ وَنَجَّيْنَٰهُمَا وَقَوْمَهُمَا مِنَ ٱلْكَرْبِ ٱلْعَظِيمِ ﴿١١٥﴾
وَنَصَرْنَٰهُمْ فَكَانُوا۟ هُمُ ٱلْغَٰلِبِينَ ﴿١١٦﴾ وَءَاتَيْنَٰهُمَا ٱلْكِتَٰبَ ٱلْمُسْتَبِينَ ﴿١١٧﴾ وَهَدَيْنَٰهُمَا ٱلصِّرَٰطَ
ٱلْمُسْتَقِيمَ ﴿١١٨﴾ وَتَرَكْنَا عَلَيْهِمَا فِى ٱلْءَاخِرِينَ ﴿١١٩﴾ سَلَٰمٌ عَلَىٰ مُوسَىٰ وَهَٰرُونَ ﴿١٢٠﴾ إِنَّا كَذَٰلِكَ
نَجْزِى ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٢١﴾ إِنَّهُمَا مِنْ عِبَادِنَا ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٢٢﴾

**114-122.** በሙሳና በሀሩን ላይ በእርግጥ ለገስን። እነርሱንም ሆነ ህዝቦቻቸውንም ከታላቅ ጭንቅ አዳንን። ረዳናቸውናም እነርሱ አሸናፊዎች ሆኑ። በጣም የተብራራውንም መጽሐፍ ሰጠናቸው። ቀጥተኛውንም መንገድ መራናቸው። በሁለቱም ላይ በኋለኞች ህዝቦች ውስጥ መልካምን ዝናን ተውንላቸው። ሰላም በሙሳና በሀሩን ላይ ይሁን። እኛ ልክ እንደዚሁ በጎ አድራጊዎችን ሁሉ እንመነዳለን። ሁለቱም በትክክል በአላህ ከአመኑት ባሮቻችን ናቸው።

وَإِنَّ إِلْيَاسَ لَمِنَ ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿١٢٣﴾ إِذْ قَالَ لِقَوْمِهِۦٓ أَلَا تَتَّقُونَ ﴿١٢٤﴾ أَتَدْعُونَ بَعْلًا وَتَذَرُونَ
أَحْسَنَ ٱلْخَٰلِقِينَ ﴿١٢٥﴾ ٱللَّهَ رَبَّكُمْ وَرَبَّ ءَابَآئِكُمُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿١٢٦﴾ فَكَذَّبُوهُ فَإِنَّهُمْ
لَمُحْضَرُونَ ﴿١٢٧﴾ إِلَّا عِبَادَ ٱللَّهِ ٱلْمُخْلَصِينَ ﴿١٢٨﴾ وَتَرَكْنَا عَلَيْهِ فِى ٱلْءَاخِرِينَ ﴿١٢٩﴾ سَلَٰمٌ عَلَىٰٓ
إِلْ يَاسِينَ ﴿١٣٠﴾ إِنَّا كَذَٰلِكَ نَجْزِى ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿١٣١﴾ إِنَّهُۥ مِنْ عِبَادِنَا ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿١٣٢﴾

**123-132.** ኢልያስም በእርግጥ ከመልዕክተኞች ነው። ለህዝቦቹ ባለ ጊዜ (አስታውስ) አላህን አትፈሩምን? በዕልን ትገዛላችሁ? ከስዓሊዎቹ ሁሉ ይበልጥ በጣም አሳማሪ የሆነውም አምላክ ትተዋላችሁን? አላህ ጌታችሁና የቀድሞዎቹ አባቶቻችሁ ጌታ ትተዋላችሁን? አስተባበሉትም ስለዚህ እነርሱ ለቅጣት የሚጣዱ ናቸው። ንፁህ የተደረጉት የአላህ ባሮች ብቻ ሲቀሩ። በእነርሱ ላይም በኋለኞቹ ህዝቦች ውስጥ መልካም ዝናን ተውንለት። ሰላም በኢልያስ ላይ ይሁን፤ እኛ እንደዚሁ መልካም ሰሪዎችን እንመነዳለን። እርሱ በእርግጥ ከምዕመናን ባሮቻችን ነው።

وَإِنَّ لُوطًا لَّمِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿١٣٣﴾ إِذۡ نَجَّيۡنَٰهُ وَأَهۡلَهُۥٓ أَجۡمَعِينَ ﴿١٣٤﴾ إِلَّا عَجُوزٗا فِي ٱلۡغَٰبِرِينَ ﴿١٣٥﴾
ثُمَّ دَمَّرۡنَا ٱلۡأٓخَرِينَ ﴿١٣٦﴾ وَإِنَّكُمۡ لَتَمُرُّونَ عَلَيۡهِم مُّصۡبِحِينَ ﴿١٣٧﴾ وَبِٱلَّيۡلِۚ أَفَلَا تَعۡقِلُونَ ﴿١٣٨﴾

**133-138.** ሉጥም በእርግጥ ከመልዕክተኞች ነው። እርሱንና ቤተሰቦቹን ሁሉንም በአዳናቸው ጊዜ (አስታውስ)። በቅጣቱ ውስጥ ከቀሪዎች የሆነችው አሮጊት ብቻ ስትቀር። ከዚያ ሌሎችን አጠፋን። (መኮች ሆይ)፣ እናንተም ያነጋችሁ ስትሆኑ በእነርሱ መኖሪያዎች ላይ በቀን ታልፉላችሁ። በሌሊትም (ታልፉላችሁ)፤ ልብም አታደርጉምን?

وَإِنَّ يُونُسَ لَمِنَ ٱلۡمُرۡسَلِينَ ﴿١٣٩﴾ إِذۡ أَبَقَ إِلَى ٱلۡفُلۡكِ ٱلۡمَشۡحُونِ ﴿١٤٠﴾ فَسَاهَمَ فَكَانَ مِنَ
ٱلۡمُدۡحَضِينَ ﴿١٤١﴾ فَٱلۡتَقَمَهُ ٱلۡحُوتُ وَهُوَ مُلِيمٞ ﴿١٤٢﴾ فَلَوۡلَآ أَنَّهُۥ كَانَ مِنَ ٱلۡمُسَبِّحِينَ ﴿١٤٣﴾ لَلَبِثَ
فِي بَطۡنِهِۦٓ إِلَىٰ يَوۡمِ يُبۡعَثُونَ ﴿١٤٤﴾ ۞ فَنَبَذۡنَٰهُ بِٱلۡعَرَآءِ وَهُوَ سَقِيمٞ ﴿١٤٥﴾ وَأَنۢبَتۡنَا عَلَيۡهِ شَجَرَةٗ
مِّن يَقۡطِينٖ ﴿١٤٦﴾ وَأَرۡسَلۡنَٰهُ إِلَىٰ مِاْئَةِ أَلۡفٍ أَوۡ يَزِيدُونَ ﴿١٤٧﴾ فَـَٔامَنُواْ فَمَتَّعۡنَٰهُمۡ إِلَىٰ حِينٖ ﴿١٤٨﴾

**139-148.** ዩኑስም በእርግጥ ከመልዕክተኞች ነው። ወደ ተመላው መርከብ በኮበለለ ጊዜ (አስታውስ)። እጣም ተጣጣለ ከተሸነፉትም ሆነ። እርሱም ተወቃሽ ሲሆን ዐሳው ዋጠው። እርሱ ለጌታው አወዳሾች ባልሆነ ኖሮ። እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ በሆዱ ውስጥ በቆየ ነበር። እርሱ በሽተኛ ሆኖ በቃይ በሌለው ባህር ዳርቻ ላይ ጣልነውም። በእርሱም ላይ በአጠገቡ ከቅል የሆነችን ዛፍ አበቀልን። ወደ መቶ ሺህ ሰዎችም ላክነው ከቶውንም ይጨምራሉ። አመኑም እስከ ጊዜ ድረስም አጣቀምናቸው።

**ከተሰላፊዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (83-148) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከአደም ጀምሮ እስከ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ድረስ ያሉት ነብያት የሚያምኑት አንድ አይነት እምነት እንደሆነ፤
2. ነብዩ ኢብራሂም የነበራቸው ቆራጥነት፤
3. ከውሸቶች ሁሉ አስከፊው ከአላህ ሌላ የማመለክ የሚል መሆኑን፤
4. መጥፎ ነገርን ማስቀረትና መከልከል የቻለ ግዴታ እንደሆነ፤
5. ነብዩ ኢብራሂም የተሞከሩት ከፍተኛ ፈተና እሳት ውስጥ እስከመታገል
6. በአላህ ዲን የሚደረጉ ትግሎች ያላቸው ክብር፤
7. ለእርድ የቀረበው የኢብራሂም ልጅ ኢስማኢል ስለመሆናቸው፤
8. ወላጆችን መታዘዝ ማክበር ግዴታ እንደሆነ፤
9. የኢብራሂምን ደረጃና ትልቅነት፤
10. የመልካም ስራ ምንዳ ከፍተኛነት
11. አላህን ለነብዩ ሙሳና ሀሩን የሰጣቸው ክብር፤
12. አላህ ለበኒ ኢስራኢል የዋለው ውለታ፤
13. ኢስላም የነብያት ሁሉ ሀይማኖት ስለመሆኑ፤
14. የእምነትና መልካም ስራ ትልቅነት
15. ሽርክን አውግዞ ተውሒድን ማፅደቅ፤
16. ከሓዲያንን አጥፍቶ አማኞችን ነፃ ማውጣት፤
17. የመልካም ስራ ትልቅነት
18. የነብዩ ሉጥን ነብይነት፤
19. ሉጥንና ተከታዩቻቸውን ነፃ አውጥቶ አስተባባዩችን ማጥፋቱን፤
20. ለቅርብ ዘመድም ቢሆን ሽምግልና ያለ አላህ ፈቃድ ምንም ጥቅም እንደሌለው።
21. በዚህች ዓለም ላይ በሚከሰቱ ነገሮች ላይ መመራመርና ከሁኔታው መማር አስፈላጊ ስለመሆኑ
22. የነብዩ ዩኑስን ነብይነት ማረጋገጥ፤
23. በባህር መርከቦች ላይ መሳፈር ተገቢ ስለመሆኑ፤
24. ችግሮችን ለመፍታት እጣ እንደሚገባ፤
25. ዚክርና ሶላት ዱዓና ተስቢህ ያለው ክብር፤
26. የነብዩ ዩኑስ ሰዎች የነበራቸው ክብር እንማራለን።

فَٱسۡتَفۡتِهِمۡ أَلِرَبِّكَ ٱلۡبَنَاتُ وَلَهُمُ ٱلۡبَنُونَ ١٤٩ أَمۡ خَلَقۡنَا ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ إِنَٰثٗا وَهُمۡ شَٰهِدُونَ ١٥٠
أَلَآ إِنَّهُم مِّنۡ إِفۡكِهِمۡ لَيَقُولُونَ ١٥١ وَلَدَ ٱللَّهُ وَإِنَّهُمۡ لَكَٰذِبُونَ ١٥٢ أَصۡطَفَى ٱلۡبَنَاتِ عَلَى
ٱلۡبَنِينَ ١٥٣ مَا لَكُمۡ كَيۡفَ تَحۡكُمُونَ ١٥٤ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ١٥٥ أَمۡ لَكُمۡ سُلۡطَٰنٞ مُّبِينٞ ١٥٦
فَأۡتُواْ بِكِتَٰبِكُمۡ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ١٥٧

**149-157.** የመካን ሰዎች ጠይቃቸውም ለጌታህ ሴት ልጆች ለእነርሱም ወንዶች ልጆች ይኖራሉ፡፡ ወይስ እኛ እነርሱ የተጣዱ ሆነው መላዕክትን ሴቶች አድርገን ፈጠርን፡፡ አስተውሉ፡፡ እነርሱ ከቅጥፈታቸው የተነሳ ይላሉ፡- አላህ መላዕክትን ወለደ እነርሱም በእርግጥ ውሸታሞች ናቸው፡፡ በወንዶች ልጆች ላይ ይልቅ ሴቶችን ልጆች መረጠን፣ ለእናንተ ምን አስረጂ አላችሁ? እንዴት ትፈርዳላችሁ! አትገነዘቡምን? ወይስ ለእናንተ ግልፅ ረጂ አላችሁን?፣ እውነተኞች እንደሆናችሁ መጽሐፍን አምጡ በላቸው፡፡

وَجَعَلُوا۟ بَيْنَهُۥ وَبَيْنَ ٱلْجِنَّةِ نَسَبًا ۚ وَلَقَدْ عَلِمَتِ ٱلْجِنَّةُ إِنَّهُمْ لَمُحْضَرُونَ ١٥٨ سُبْحَـٰنَ ٱللَّهِ
عَمَّا يَصِفُونَ ١٥٩ إِلَّا عِبَادَ ٱللَّهِ ٱلْمُخْلَصِينَ ١٦٠ فَإِنَّكُمْ وَمَا تَعْبُدُونَ ١٦١ مَآ أَنتُمْ عَلَيْهِ
بِفَـٰتِنِينَ ١٦٢ إِلَّا مَنْ هُوَ صَالِ ٱلْجَحِيمِ ١٦٣

**158-163.** በአላህና በአጋንንት መካከልም ዝምድናን አደረጉ፡፡ አጋንንትም ሆኑ ይህን ባዩች በእሳት የሚጣዱ መሆናቸውን በእርግጥ አውቀዋል፡፡ አላህ ከሚመጥኑት ሁሉ ጠራ፡፡ ግን የመረጡት የአላህ ባሮች በአላህ ላይ አይዋሹም፡፡ (ካሐዲያን ሆይ)፣ እናንተም የምትገዟቸውም ሁሉ፤ በእርሱ በአላህ ላይ አንድንም አጥማሚዎች አይደላችሁም ያንን እርሱ ገሀነም ገቢ የሆነውን ሰው ቢሆን እንጂ፡፡

ከተሰላፊዎች ምዕራፍ (158) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰሊም፤ ኹዛዓ፤ ጁሃይና በተባሉ ብሄሮች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው የሚሉ ሰዎች ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ ቁረይሽ መላይኮች ማለት የአላህ ሴት ልጆች ናቸው በማለት ሲናገሩ አቡበክር ሲዲቅ እናቶቻቸውስ እነማን ናቸው በማለት ሲጠይቁ የምርጥ ጅን ልጆች ናቸዋ በማለታቸው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ሱዩጢ)

وَمَا مِنَّآ إِلَّا لَهُۥ مَقَامٌ مَّعْلُومٌ ١٦٤ وَإِنَّا لَنَحْنُ ٱلصَّآفُّونَ ١٦٥ وَإِنَّا لَنَحْنُ ٱلْمُسَبِّحُونَ ١٦٦

**164-166.** (ጅብሪል አለ) ከእኛ አንድም የለም፤ ለእርሱ የታወቀ ደረጃ ያለው ቢሆን እንጅ፡፡ እኛም ጌታን ለመገዛት ተሰላፊዎቹ እኛ ነን፡፡ እኛም አላህን አጥሪዎቹ እኛ ብቻ ነን፡፡

وَإِن كَانُوا۟ لَيَقُولُونَ ١٦٧ لَوْ أَنَّ عِندَنَا ذِكْرًا مِّنَ ٱلْأَوَّلِينَ ١٦٨ لَكُنَّا عِبَادَ ٱللَّهِ
ٱلْمُخْلَصِينَ ١٦٩ فَكَفَرُوا۟ بِهِۦ ۖ فَسَوْفَ يَعْلَمُونَ ١٧٠ وَلَقَدْ سَبَقَتْ كَلِمَتُنَا لِعِبَادِنَا
ٱلْمُرْسَلِينَ ١٧١ إِنَّهُمْ لَهُمُ ٱلْمَنصُورُونَ ١٧٢ وَإِنَّ جُندَنَا لَهُمُ ٱلْغَـٰلِبُونَ ١٧٣

**167-173.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱ (ከሓዲያን) በእርግጥ ይሉ ነበር። ከቀደሞዎቹ መጽሐፍ ገሳጭ መጽሐፍ እኛ ዘንድ በነበረ ኖሮ የአላህ ምርጦች ባሮች በሆን ነበር። ግን ቁርአኑ በመጣላቸው ጊዜ በእርሱ ላይ ካዱ ወደ ፊትም በእርግጥ ያውቃሉ። የእርዳታ ቃላችንም መልዕክተኞች ለሆኑት ባሮቻችን በእውነት አልፋለች። እነርሱ ተረጂዎች እነርሱ ናቸው። ሰራዊቶቻችንም በእርግጥ አሸናፊዎች እነርሱ ናቸው።

فَتَوَلَّ عَنْهُمْ حَتَّىٰ حِينٍ ﴿١٧٤﴾ وَأَبْصِرْهُمْ فَسَوْفَ يُبْصِرُونَ ﴿١٧٥﴾ أَفَبِعَذَابِنَا يَسْتَعْجِلُونَ ﴿١٧٦﴾
فَإِذَا نَزَلَ بِسَاحَتِهِمْ فَسَاءَ صَبَاحُ ٱلْمُنذَرِينَ ﴿١٧٧﴾

**174-177.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱም ከመካ ከሓዲያን እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስ ዙር ተዋቸው። ተመልከታቸውም ወደፊትም የሚደርስባቸውን ያያሉ። በቅጣታችንም ያቻኩሉናል በቀያቸውም በወረደ ጊዜ የተስፈራሪዎች ንጋት ከፋ!

وَتَوَلَّ عَنْهُمْ حَتَّىٰ حِينٍ ﴿١٧٨﴾ وَأَبْصِرْ فَسَوْفَ يُبْصِرُونَ ﴿١٧٩﴾ سُبْحَٰنَ رَبِّكَ رَبِّ ٱلْعِزَّةِ عَمَّا
يَصِفُونَ ﴿١٨٠﴾ وَسَلَٰمٌ عَلَى ٱلْمُرْسَلِينَ ﴿١٨١﴾ وَٱلْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٨٢﴾

**178-182.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱን እስከ ጥቂት ጊዜ ድረስ ተዋቸው። ተመልከትም በእርግጥም ያያሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የማሸነፊፍ ጌታ የሆነው ጌታህ ከሚሉት ሁሉ ጠራ። በመልዕክተኞችም ላይ ሰላም ይሁን። ምስጋና ሁሉም ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይገባው።

**ከተሰላፊዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (149-182) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መልአክን የአላህ ሴት ልጆች ናቸው የሚሉት በኒሚልሓን የተባሉ ብሄረሰቦች የቀጠፉት ቅጥፈት፤
2. ውሸትን በከባድ ማስረጃ መቃወም ተገቢ ስለ መሆኑ፤
3. ጠንካራ ማስረጃ ማለት ከቁርአንና ከሃዲስ የሆነ ብቻ እንደሆነ
4. የቀድርን እውነትነት ማረጋገጥ፤
5. መላኢኮች የአላህ ባህሪ ስለ መሆናቸው፤
6. በሶላት ሰልፉን ማስተካከል አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
7. የአጋሪዎችን ቅጥፈት ማጋለጥ፤
8. አጋሪዎችን ለመቅጣት መዛቱን
9. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
10. አላህ ለመልዕክተኛው ለነብዩ (ﷺ) ለመርዳት ቃል መግባቱ፤
11. ዱዓንም ሆነ ሌላውን ዚክር ሱብሃነ ረቢከ... በሚል መደምደሙ ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የተሰላፊዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (38)
# የሷድ ምዕራፍ
# (ሱረቱ ሷድ)

سُورَةُ صٓ

## በመካ ነው የወረደው። የአናቅፁ ብዛት (88) ናቸው።
## የሱረቱ ሷድ መግቢያ

መካዊ እንደ መሆኑ ሁሉ ሶስት ዋና ዋና ነገሮች ላይ ማለትም፡

1. በአላህ አንድነት፤
2. በሙቶ መነሳት ሐቅነትና፤
3. ስለ ወህይ ምንነት ያስተምራል። አስተምህሮቱን ሲጀምር የታላቁ ቁርኣንን እውነትነት፤ የነብዩ (ﷺ) ነብይነትን ትክክለኛ መሆኑን በመሐላ በማረጋገጥ ነው። የአላህን አንድነት በሰፊው አስተምሮ ይህን እውነታ የካዱ ሁሉ በስህተት ላይ እንደሆኑ ያጋልጣል። በተጨማሪም ያለፉት ከሓዲያን የደረሰባቸው አይነት እንዳይደርስባቸው ያስጠነቅቃል። ነብዩን (ﷺ) ለማፅናናት የአያሌ ነብያትን ታሪክም ዘርዝሯል። በተለይ የነብዩ ዳዉድንና የነብዩ ሱለይማንን ታሪኮች አንስቶ የደረሰባቸዉን ፈተና በሰፊው ይተነትናል።

የነብዩ አዩብን ፈተናም በሰፊው አውስቷል። የኢስሓቅን፤ የየዕቁብን፤ የኢስማኢልንና የዙልኪፍልንም (عليه السلام) ታሪክ በአጭሩ አውስቶ በስተመጨረሻም የነብያት ተልዕኮ ምን እንደሆነ በመግለፅ እና ከዚያ የነብዩን (ﷺ) ዋና ዋና መልዕክት በማብራራት ነው የሚያጠቃልለው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

صٓۚ وَٱلۡقُرۡءَانِ ذِي ٱلذِّكۡرِ ١ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي عِزَّةٖ وَشِقَاقٖ ٢
كَمۡ أَهۡلَكۡنَا مِن قَبۡلِهِم مِّن قَرۡنٖ فَنَادَواْ وَّلَاتَ حِينَ مَنَاصٖ ٣

**1-3.** *ሷድ፤ የክብር ባለቤት በሆነው ቁርኣን እምላለሁ። (ጉዳዩ ብዙ አማልክት አሉ እንደሚሉት አይደለም)። ይልቁንም እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች በከባድ ትዕቢትና በአጓጉል ክርክር ውስጥ ናቸው። ከእነርሱ በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች ብዙን አጥፍተናል። ጊዜው የመሸሻና የማምለጫ ጊዜ ሳይሆንም (ለእርዳታ) ተጣሩ።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَعَجِبُوٓاْ أَن جَآءَهُم مُّنذِرٞ مِّنۡهُمۡۖ وَقَالَ ٱلۡكَٰفِرُونَ هَٰذَا سَٰحِرٞ كَذَّابٌ ٤ أَجَعَلَ ٱلۡأٓلِهَةَ
إِلَٰهٗا وَٰحِدًاۖ إِنَّ هَٰذَا لَشَيۡءٌ عُجَابٞ ٥ وَٱنطَلَقَ ٱلۡمَلَأُ مِنۡهُمۡ أَنِ ٱمۡشُواْ وَٱصۡبِرُواْ عَلَىٰٓ
ءَالِهَتِكُمۡۖ إِنَّ هَٰذَا لَشَيۡءٞ يُرَادُ ٦ مَا سَمِعۡنَا بِهَٰذَا فِي ٱلۡمِلَّةِ ٱلۡأٓخِرَةِ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا
ٱخۡتِلَٰقٌ ٧ أَءُنزِلَ عَلَيۡهِ ٱلذِّكۡرُ مِنۢ بَيۡنِنَاۚ بَلۡ هُمۡ فِي شَكّٖ مِّن ذِكۡرِيۚ بَل لَّمَّا يَذُوقُواْ
عَذَابِ ٨ أَمۡ عِندَهُمۡ خَزَآئِنُ رَحۡمَةِ رَبِّكَ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡوَهَّابِ ٩ أَمۡ لَهُم مُّلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَاۖ فَلۡيَرۡتَقُواْ فِي ٱلۡأَسۡبَٰبِ ١٠ جُندٞ مَّا هُنَالِكَ مَهۡزُومٞ مِّنَ ٱلۡأَحۡزَابِ ١١

**4-11.** ከእነርሱ መካከል የሆነ አስፈራሪ ስለመጣላቸው ተደነቁ። ከሓዲያንም ይህ ድግምተኛ ጠንቋይ ውሸታም ነው አሉ። አማልዕክቶችን አንድ አምላክ አደረጋቸውን? ይህ አስደናቂ ነገር ነው አሉ። ከእነርሱም መካከል ባለአባቶች በሉ ሂዱ በአማልክቶቻችሁም መገዛት ላይ ፅኑ። ይህ ከእኛ የሚፈለግ ነገር ነውና እያሉ አዘገሙ። ይህንንም አስተምህሮት ከኋለኛይቱ (ከመጨረሻይቱ) ሃይማኖት አልሰማንም። ይህ ውሸትን መፍጠር እንጂ ሌላ አይደለም እያሉም አዘገሙ። ከመካከላችን ከእርሱ ላይ ብቻ ቁርኣን ተወረደን? አሉ። በእውነት እነርሱ ከግሳጼየ በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። በእርግጥም ቅጣትን ገና አልቀመሱም። ለመሆኑ የአሸናፊውና የለጋሹ ጌታህ የአላህ የችሮታው መካዚኖች እነርሱ ዘንድ ናቸውን? ወይስ የሰማይ የምድር እና የመካከላቸውም ንግስና የእነርሱ ነውን? ነው ካሉ እስቲ በመሰላሎች ወደ ላይ ይውጡ። እነርሱም እዚያ ዘንድ ከአህዛብ ሁሉ ተሸናፊ የሆነ ሰራዊት ናቸው።

ከሷድ ምዕራፍ ከ (1-11) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡-

አቡ ጧሊብ ታመው በነበሩበት ወቅት ነብዩ (ﷺ) አጠገባቸው መጥተው ላኢለህ ኢለላህ እንዲሉ እየጣሩ ባሉበት በአጠገባቸው አቡጀህልን የጨመረ የመኮች ቡድን ነበረና እባክህ አቡ ጧሊብ ይህን ሰው ከልክልልን ስለአላቸው አቡጧሊብም የወንድሜ ልጅ ከዘመዶችህ ምንድ ነው መውሰድ የምትፈልገው ሲሏቸው አጎቴ ሆይ! ከእነሱ የምፈልግባቸው ነገር አንዲት ቃል ብቻ ነው አሏቸው እነሱ ለመሆኑ ምን አይነት ቃል ናት አሏቸው። እሳቸውም ላኢለህ ኢለሏህ ናት አሉ በዚህን ጊዜ ያን ሁሉ አምላክ ሰርዘህ አንድ አምላክ ተገዙ አልክ አንጼ በማለት ሲገርሙ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። ዋሒዲ እና ሱዩጢ።

كَذَّبَتۡ قَبۡلَهُمۡ قَوۡمُ نُوحٖ وَعَادٞ وَفِرۡعَوۡنُ ذُو ٱلۡأَوۡتَادِ ١٢ وَثَمُودُ وَقَوۡمُ لُوطٖ وَأَصۡحَٰبُ
لۡـَٔيۡكَةِۚ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلۡأَحۡزَابُ ١٣ إِن كُلٌّ إِلَّا كَذَّبَ ٱلرُّسُلَ فَحَقَّ عِقَابِ ١٤ وَمَا يَنظُرُ هَٰٓؤُلَآءِ
إِلَّا صَيۡحَةٗ وَٰحِدَةٗ مَّا لَهَا مِن فَوَاقٖ ١٥ وَقَالُواْ رَبَّنَا عَجِّل لَّنَا قِطَّنَا قَبۡلَ يَوۡمِ ٱلۡحِسَابِ ١٦

**12-16.** ከእነርሱም በፊት የኑህ ህዝቦች፤ ዓድ እና የችካሎች ባለቤት የሆነው ፈርዖንም አስተባበሉ። ሰሙድም፤ የሉጥ ሰዎችም፤ የአይካ* ሰዎችም፤ አስተባበሉ። እነዚህ አህዛቦች ናቸው። ሁሉም መልዕክተኞችን ያስዋሹ እንጂ ሌላ አይደሉም። ከዚያ ቅጣቴ ተረጋገጠባቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚህ ለእርሷ መመለስ የሌላት አንዲት ጩኸት እንጂ ሌላን አይጠባበቁም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሚሉት ነገር ላይ ታገስ። የኃይል ባለቤት የሆነውን ባሪያችንም ዳውድንም አውሳላቸው። እርሱ በጣም መላሳ ነበርና።

* በአል ሒጅር ምዕራፍ (78) ኛው አንቀጽ ከታች የተጻፈውን ተመልከት።

ٱصۡبِرۡ عَلَىٰ مَا يَقُولُونَ وَٱذۡكُرۡ عَبۡدَنَا دَاوُۥدَ ذَا ٱلۡأَيۡدِۖ إِنَّهُۥٓ أَوَّابٌ ﴿١٧﴾ إِنَّا سَخَّرۡنَا ٱلۡجِبَالَ
مَعَهُۥ يُسَبِّحۡنَ بِٱلۡعَشِيِّ وَٱلۡإِشۡرَاقِ ﴿١٨﴾ وَٱلطَّيۡرَ مَحۡشُورَةٗۖ كُلّٞ لَّهُۥٓ أَوَّابٞ ﴿١٩﴾ وَشَدَدۡنَا مُلۡكَهُۥ
وَءَاتَيۡنَٰهُ ٱلۡحِكۡمَةَ وَفَصۡلَ ٱلۡخِطَابِ ﴿٢٠﴾

**17-20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሚሉት ነገር ላይ ታገስ። የሃኃይል ባለቤት የሆነውን ባሪያችንንም ዳውድን አውሳው። እርሱ በጣም መላሳ ነው። እኛ ተራራዎችን ከቀትር በኋላና በረፋዱም ከእነርሱ ጋር የሚያወድሱ ሲሆን እንዲታዘዙት አገራንለት። በራሪዎችንም (አእዋፍን) የሚሰበሰቡ ሆነው አገራንለት። ሁሉም ለእርሱ ማወደስ የሚመላለስ ነው። መንግስትነትንም አበረታንለት ጥበብንም ንግግርን መለየትንም ሰጠነው።

۞ وَهَلۡ أَتَىٰكَ نَبَؤُاْ ٱلۡخَصۡمِ إِذۡ تَسَوَّرُواْ ٱلۡمِحۡرَابَ ﴿٢١﴾ إِذۡ دَخَلُواْ عَلَىٰ دَاوُۥدَ فَفَزِعَ مِنۡهُمۡۖ
قَالُواْ لَا تَخَفۡۖ خَصۡمَانِ بَغَىٰ بَعۡضُنَا عَلَىٰ بَعۡضٖ فَٱحۡكُم بَيۡنَنَا بِٱلۡحَقِّ وَلَا تُشۡطِطۡ وَٱهۡدِنَآ
إِلَىٰ سَوَآءِ ٱلصِّرَٰطِ ﴿٢٢﴾ إِنَّ هَٰذَآ أَخِي لَهُۥ تِسۡعٞ وَتِسۡعُونَ نَعۡجَةٗ وَلِيَ نَعۡجَةٞ وَٰحِدَةٞ فَقَالَ
أَكۡفِلۡنِيهَا وَعَزَّنِي فِي ٱلۡخِطَابِ ﴿٢٣﴾ قَالَ لَقَدۡ ظَلَمَكَ بِسُؤَالِ نَعۡجَتِكَ إِلَىٰ نِعَاجِهِۦۖ وَإِنَّ
كَثِيرٗا مِّنَ ٱلۡخُلَطَآءِ لَيَبۡغِي بَعۡضُهُمۡ عَلَىٰ بَعۡضٍ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَقَلِيلٞ
مَّا هُمۡۗ وَظَنَّ دَاوُۥدُ أَنَّمَا فَتَنَّٰهُ فَٱسۡتَغۡفَرَ رَبَّهُۥ وَخَرَّۤ رَاكِعٗاۤ وَأَنَابَ۩ ﴿٢٤﴾ فَغَفَرۡنَا لَهُۥ ذَٰلِكَۖ
وَإِنَّ لَهُۥ عِندَنَا لَزُلۡفَىٰ وَحُسۡنَ مَـَٔابٖ ﴿٢٥﴾

**21-25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የተከራካሪዎቹ ወሬ መጥቶልሃልን? ሚህራቡን (ምኩራብን) በተንጠላጠሉ ጊዜ። በዳውድ ላይም በገቡ ጊዜ ከእነርሱም ሁኔታ በደነገጠ ጊዜ አትፍራ እኛ ከፊላችን በከፊሉ ላይ ወሰን ያለፈ ሁለት ተከራካሪዎች ነን በመካከላችንም በእውነት ፍረድ አታዳላም ወደ ትክክለኛው መንገድ ምራን አሉት። ይህ ወንድሜ ነው። ለእነርሱ ዘጠና ዘጠኝ ሴቶች በጎች አሉት ለእኔም አንዷት ሴት በግ አለችኝ እርሷም እድሌ አድርጋት አለኝ። በንግግርም አሸነፈኝ አለው። ሴት በግህን ወደ በጎች ለመቀላቀል በመጠየቁ በእርግጥ በደለህ ከተጋሪዎች ብዙዎቹ ከፊላቸው በከፊሉ ላይ ወሰን ያልፋሉ። እነዚያ ያመኑትና መልካሞችን የሰሩት ብቻ ሲቀሩ እነርሱም በጣም ጥቂቶች ናቸው አለ። ዳውድም የፈተንነው መሆኑን ወዲያዉኑ አወቀ። ከጌታውም ምህረትን ለመነና ሰጋጅ ሆኖ ወደቀም በመፀፀትም ተመለሰ። ለእርሱ ለእኛ ዘንድ የመቅረብ ክብር መልካም መመለሻም አለው።

**ከሷድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-25) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ በፈለገው መማል እንደሚችል፤
2. የመካ ከሓዲያን የነበራቸው ትዕቢትና ለነቢዩ ነብዩ (ﷺ) የነበራቸው ጥላቻ ምን እንደሚመስል፤
3. ላኢላሀኢለሏህን በመካድ መኮች የደረሰባቸውን ድንቁርና፤
4. አጋሪዎች ለአላህ ያሳዩት ፍልሚያ፤
5. ቁርአን የተናገራቸው ገይብና ተፈፃሚነታቸውን በገሀድ ማየትን፤
6. ነብዩን (ﷺ) ቀደምት ነብያትን ተመሳሳይ ታሪክ በማውሳት ማፅናናት፤
7. ቁረይሾችን ማስፈራራትና ማፅናናት፤
8. አጋሪዎች እንዴት በአላህ ህግ ያፌዙ እንደነበር፤
9. በመልካም ሰዎች አርአያ ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ፤
10. አላህ ለነብዩ ዳውድ ጋራንና በራሪዎችን እንዴት እንዳናገራቸው፤
11. የነብዩ ዳውድ ድምፅ ምን ያምር እንደነበር፤
12. የአዱሓ ሶላትን መስገድ ተገቢ ስለመሆኑ፤
13. አላህ ለነብዩ ዳውድ የቸራቸውን ትዕግስት ሰዎች ሳያስፈቅዷቸው ወደቤታቸው ሲገቡ ያለምንም ቅሬታ ማስተናገዳቸው፤
14. ለባለ ስልጣኖችም ቤት ይሁን በሌሎች ሰዎች ቤት ሲገባ ስርአት ሊኖረው እንደሚገባ፤
15. የባለ ጉዳዩ ስርኣት አልበኝነት ዳኞችን ጉዳዩን በፍትህ እንዲያዩት እንደሚገባ፤
16. ነብዩ ዳውድ አብዛሀኙን ሰዓት የሚያሳልፉትን በሚህራባቸው እንደነበር፤
17. አላህ ለሰዎች ከሚውልላቸው ውለታዎች መካከል ዋናው ጠቃሚ እውቀት መሆኑን፤
18. አላህ ነብያችን (ﷺ) እንደሚንከባከባቸውና ለስህተት ሲጋለጡ ወዲያውኑ የሚስተካከሉበትን ተግባር እንደሚወፍቃቸው፤
19. ከሁሉም ነገር ወደ አላህ መመለስ የነብያት ተግባር መሆኑንና ማንም ሙስሊም ይህን አርአያ መከተል እንዳለበት፤
20. አላህ በዒባዳ ላይ ጠንካራን እንደሚወድ፤

21. በሰዎች መካከል ውሳኔን መስጠት ኃይማኖታዊ ጉዳይ መሆኑን ይህንንም ተግባር ነብያት የመጀመሪያ ተግባሪው አድርጎውት የነበረ ሲሆን ለዚህም ኃይማታዊ እውቀት የጉዳዩንም ዝርዝር ማወቅ በጣም አስፈላጊ መሆኑን፤
22. በሰዎች መካከል ውሳኔን ለመስጠት የተሰየመ ሰው ስሜትን፤ ወገናዊነትንና የግል ጥቅምን ማራቅ እንዳለበት፤
23. ነብዩ ሱለይማን ራሳቸው አላህ ስለ ነብዩ ዳውድ የሰጣቸው ትሩፋት መሆናቸውንና አላህ ለባሮቹ ከሚቸራቸው ታላቅ ፀጋዎች መካከል መልካም ልጅ መስጠቱ መሆኑን፤
24. ነብዩ ሱለይማን የአላህን ውዴታና ፍላጎት ከግል ስሜት ማስቀደማቸውን፤
25. አንድን ነገር ለአላህ ብሎ የተወ ሰው አላህ ከተወው በተሻለ እንደሚሰጠው፤
26. ሰይጣንን እንደልብ ማዘዝ ከነብዩ ሱለይማን በኋላ ማንም እንደማይችል
27. እንዲህ ያሉ ታሪኮችን በማቅረብ መፅናናት፤
28. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
29. መላኢኮች በአደም ልጆች መመሰል እንደሚችሉ እና ከሁለቱም ሳይሰማ መወሰን እንደሌለብን፤
30. በወንጀል ላይ የወደቁ ሰዎች ወዲያው ተውባህ ማድረግ እንዳለባቸው እንማራለን።

يَٰدَاوُۥدُ إِنَّا جَعَلۡنَٰكَ خَلِيفَةٗ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَٱحۡكُم بَيۡنَ ٱلنَّاسِ بِٱلۡحَقِّ وَلَا تَتَّبِعِ ٱلۡهَوَىٰ فَيُضِلَّكَ
عَن سَبِيلِ ٱللَّهِۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَضِلُّونَ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ لَهُمۡ عَذَابٞ شَدِيدُۢ بِمَا نَسُواْ يَوۡمَ ٱلۡحِسَابِ ٢٦

**26.** ዳውድ ሆይ፣ እኛ በምድር ላይ ምትክ አድርገንሀልና በሰዎች መካከል በእውነት ፍረድ። የግል ዝንባሌህንም አትከተል። ከአላህ መንገድ ያሳስተሃልና። እናም እነዚያ ከአላህ መንገድ የሚሳሳቱ ሁሉ የምርመራውን ቀን በመርሳታቸው ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አለባቸው።

وَمَا خَلَقۡنَا ٱلسَّمَآءَ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَا بَٰطِلٗاۚ ذَٰلِكَ ظَنُّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْۚ فَوَيۡلٞ لِّلَّذِينَ
كَفَرُواْ مِنَ ٱلنَّارِ ٢٧

**27.** ሰማይን ምድርና በመካከላቸውም ያለውን ሁሉ ለከንቱ አልፈጠርንም። ይህ የእነዚያ የካዱት ሰዎች ጥርጣሬ ነው። ለእነዚያም ለካዱት ሰዎች ሁሉ ከእሳት ወዮውላቸው።

أَمۡ نَجۡعَلُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ كَٱلۡمُفۡسِدِينَ فِي ٱلۡأَرۡضِ
أَمۡ نَجۡعَلُ ٱلۡمُتَّقِينَ كَٱلۡفُجَّارِ ٢٨

**28.** በእውነቱ እነዚያ በትክክል ያመኑትና መልካም ተግባሮችን የሰሩት ሰዎች ልክ በምድር ውስጥ እንደሚያጠፉት እናደርጋለን? ወይንስ አላህን ፈሪዎችን ልክ እንደ ከሓዲያን እናደርጋለን?።

كِتَٰبٌ أَنزَلۡنَٰهُ إِلَيۡكَ مُبَٰرَكٞ لِّيَدَّبَّرُوٓاْ ءَايَٰتِهِۦ وَلِيَتَذَكَّرَ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٢٩

29. ይህ መጽሀፍ ወደ አንተ ያወረድነው ብሩክ መጽሀፍ ነው። አናቅፅን እንዲያስተነትኑና የአእምሮ ባላቤቶች እንዲገሰፁበት አወረድነው።

وَوَهَبۡنَا لِدَاوُۥدَ سُلَيۡمَٰنَۚ نِعۡمَ ٱلۡعَبۡدُ إِنَّهُۥٓ أَوَّابٌ ٣٠ إِذۡ عُرِضَ عَلَيۡهِ بِٱلۡعَشِيِّ ٱلصَّٰفِنَٰتُ ٱلۡجِيَادُ ٣١ فَقَالَ إِنِّيٓ أَحۡبَبۡتُ حُبَّ ٱلۡخَيۡرِ عَن ذِكۡرِ رَبِّي حَتَّىٰ تَوَارَتۡ بِٱلۡحِجَابِ ٣٢ رُدُّوهَا عَلَيَّۖ فَطَفِقَ مَسۡحَۢا بِٱلسُّوقِ وَٱلۡأَعۡنَاقِ ٣٣ وَلَقَدۡ فَتَنَّا سُلَيۡمَٰنَ وَأَلۡقَيۡنَا عَلَىٰ كُرۡسِيِّهِۦ جَسَدٗا ثُمَّ أَنَابَ ٣٤ قَالَ رَبِّ ٱغۡفِرۡ لِي وَهَبۡ لِي مُلۡكٗا لَّا يَنۢبَغِي لِأَحَدٖ مِّنۢ بَعۡدِيٓۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡوَهَّابُ ٣٥ فَسَخَّرۡنَا لَهُ ٱلرِّيحَ تَجۡرِي بِأَمۡرِهِۦ رُخَآءً حَيۡثُ أَصَابَ ٣٦ وَٱلشَّيَٰطِينَ كُلَّ بَنَّآءٖ وَغَوَّاصٖ ٣٧ وَءَاخَرِينَ مُقَرَّنِينَ فِي ٱلۡأَصۡفَادِ ٣٨ هَٰذَا عَطَآؤُنَا فَٱمۡنُنۡ أَوۡ أَمۡسِكۡ بِغَيۡرِ حِسَابٖ ٣٩ وَإِنَّ لَهُۥ عِندَنَا لَزُلۡفَىٰ وَحُسۡنَ مَـَٔابٖ ٤٠

30-40. ለዳውድ ሱለይማንን ሰጠነው። (ሱለይማን) ምን ያምር ባሪያ ነው። እርሱ ወደ ጌታው መላሳ ነውና። በእርሱ ላይ ከቀትር በኋላ በሶስት እግሮችና በአራተኛው እግር ኮቴ ጫፍ የሚቆሙ ጮሌ ፈረሶች በተቀረቡበት ጊዜ (የሆነዉን አስታውስ)። እኔ ፀሀይ በግርዶ እስከተደበቀች ድረስ ጌታየን ከማስታወስ ፈንታ ፈረስን መውደድን መረጥኩ። በሉ ፈረሶችን ወደ እኔ መልሷቸው (አለ)። ከዚያ እግሮቻቸዉንና አንገቶቻቸዉን ማበስ (መቁረጥ) ያዘ*። ሱለይማንን በእርግጥ በፈረሶች ፈተንነው። በወንበሩም ላይ የሆነ አካልን ጣልን። ከዚያ በመፀፀት ተመለሰ። ጌታዬ ሆይ፣ ማረኝ ከእኔ በኋላ ለአንድም የማይገባን ንግስናንም ስጠኝ። ለጋሹ አንተ ብቻ ነህና አለ። ንፋስንም በትዕዛዙ ወደ ፈለገበት ስፍራ ልዝብ ሆና የምትነፍስ ስትሆን ገራንለት። ሰይጣናትንም ገንቢዎችንና ሰማጮችን ሁሉ ገራንለት። ሌሎችንም በፍንጆች ተቆራኞችን ገራንለት። ይህ ስጦታችን ነው ያለ ግምት ለግስ። ወይም ጨብጥ (አል ነው)። ለእርሱም እኛ ዘንድ መቅረብ መልካም መመለሻ በእርግጥ አለው።

* አበሱ በሚለው ቃል ዙሪያ ብዙ አባባል ያለ ቢሆንም የተመረጠው አረዳቸው ማለት ነው የሚለውን ነው።

وَٱذْكُرْ عَبْدَنَآ أَيُّوبَ إِذْ نَادَىٰ رَبَّهُۥٓ أَنِّى مَسَّنِىَ ٱلشَّيْطَٰنُ بِنُصْبٍ وَعَذَابٍ ﴿٤١﴾ ٱرْكُضْ بِرِجْلِكَ ۖ هَٰذَا
مُغْتَسَلٌۢ بَارِدٌ وَشَرَابٌ ﴿٤٢﴾ وَوَهَبْنَا لَهُۥٓ أَهْلَهُۥ وَمِثْلَهُم مَّعَهُمْ رَحْمَةً مِّنَّا وَذِكْرَىٰ لِأُو۟لِى ٱلْأَلْبَٰبِ ﴿٤٣﴾
وَخُذْ بِيَدِكَ ضِغْثًا فَٱضْرِب بِّهِۦ وَلَا تَحْنَثْ ۗ إِنَّا وَجَدْنَٰهُ صَابِرًا ۚ نِّعْمَ ٱلْعَبْدُ ۖ إِنَّهُۥٓ أَوَّابٌ ﴿٤٤﴾

**41-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባሪያችን አዩብንም (እዮብንም) አወሳላቸው። እኔ ሰይጣን በጉዳትና በስቃይ ነካኝ ሲል ጌታው በተጣራ ጊዜ። በእግርህ ምድርን ምታ። ይህ ቀዝቃዛ መታጠቢያ መጠጥም ነው (ተባለ)። ለእርሱም ከእኛ ዘንድ ለችሮታ ባለ አእምሮዎችንም ለመገሰፅ ቤተሰቦቹንም ከእነርሱ ጋር መሰላቸውን ሰጠነው። በእጅህ ጨብጥ አርጬሜን ያዝ በእርሱም (ሚስትህን) ምታ ማላህንም አታፍርስ (አልነው)። እነሆ እና ታጋሽ ሆኖ አገኘነው ምን ያምር ባሪያ ነው። እርሱም በጣም መላሳ ነው።

وَٱذْكُرْ عِبَٰدَنَآ إِبْرَٰهِيمَ وَإِسْحَٰقَ وَيَعْقُوبَ أُو۟لِى ٱلْأَيْدِى وَٱلْأَبْصَٰرِ ﴿٤٥﴾ إِنَّآ أَخْلَصْنَٰهُم
بِخَالِصَةٍ ذِكْرَى ٱلدَّارِ ﴿٤٦﴾ وَإِنَّهُمْ عِندَنَا لَمِنَ ٱلْمُصْطَفَيْنَ ٱلْأَخْيَارِ ﴿٤٧﴾

**45-47.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ባሮቻችንም ኢብራሂምን ኢስሐቅንና ያዕቆብንም የኃይልና የማስተዋል ባለቤቶች የሆኑትን አውሳላቸው። እኛ ጥሩ በሆነች ጠባይ መረጥናቸው፤ እርሷም የመጨረሻይቱ አገር ማስታወስ ናት። እነርሱም እኛ ዘንድ ከመልካሞቹ ምርጦች ናቸው።

وَٱذْكُرْ إِسْمَٰعِيلَ وَٱلْيَسَعَ وَذَا ٱلْكِفْلِ ۖ وَكُلٌّ مِّنَ ٱلْأَخْيَارِ ﴿٤٨﴾
هَٰذَا ذِكْرٌ ۚ وَإِنَّ لِلْمُتَّقِينَ لَحُسْنَ مَـَٔابٍ ﴿٤٩﴾

**48-49.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢስማኢልንም፤ ኢልያስንም፤ ዙልኪፍልንም አውሳ፤ ሁሉም ከነቢያት ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህ መልካም ዝና ነው። ለአላህ ፈሪዎችም በእርግጥ ውብ የሆነ መመለሻ አላቸው።

جَنَّٰتِ عَدْنٍ مُّفَتَّحَةً لَّهُمُ ٱلْأَبْوَٰبُ ﴿٥٠﴾ مُتَّكِـِٔينَ فِيهَا يَدْعُونَ فِيهَا بِفَٰكِهَةٍ كَثِيرَةٍ
وَشَرَابٍ ﴿٥١﴾ ۞ وَعِندَهُمْ قَٰصِرَٰتُ ٱلطَّرْفِ أَتْرَابٌ ﴿٥٢﴾ هَٰذَا مَا تُوعَدُونَ لِيَوْمِ ٱلْحِسَابِ ﴿٥٣﴾
إِنَّ هَٰذَا لَرِزْقُنَا مَا لَهُۥ مِن نَّفَادٍ ﴿٥٤﴾ هَٰذَا ۚ وَإِنَّ لِلطَّٰغِينَ لَشَرَّ مَـَٔابٍ ﴿٥٥﴾

**50-55.** በሮቻቸው ለእነርሱ የተከፈቱ ሲሆኑ የመኖሪያ ገነቶች አሏቸው። በእርሷ ውስጥ የተደገፉ ሆነው በውስጧ በብዙ እሸቶችና በመጠጥም ያዝዛሉ። እነርሱ ዘንድ ዓይኖቻቸውን በባሎቻቸው ላይ አሳጣሪዎች እኩያዎች ሴቶች አሉ። ይህ ለምርመራው ቀን የምትቀጠሩት ተስፋ ነው። ይህ ሲሳያችን ነው። ለእርሱ ምንም ማለቅ የለውም። ይህ (ለምእመናን ነው) ለጠማሞችም በጣም የከፋ መመለሻ አላቸው።

جَهَنَّمَ يَصْلَوْنَهَا فَبِئْسَ ٱلْمِهَادُ ﴿٥٦﴾ هَٰذَا فَلْيَذُوقُوهُ حَمِيمٌ وَغَسَّاقٌ ﴿٥٧﴾ وَءَاخَرُ مِن شَكْلِهِۦٓ أَزْوَٰجٌ ﴿٥٨﴾ هَٰذَا فَوْجٌ مُّقْتَحِمٌ مَّعَكُمْ لَا مَرْحَبًۢا بِهِمْ إِنَّهُمْ صَالُوا۟ ٱلنَّارِ ﴿٥٩﴾

**56-59.** የሚገቧት ስትሆን ገሀነም አለቻቸው። ምንጣፊቱም ምንኛ ከፋች። ይህ ለከሓዲያን ነው። ይቅመሱትም የፈላ ውሃ እዥ ነው። ሌላም እነርሱን ከመሰሉ ብዙ አይነቶች አሉ። ይህ ከናንተ ጋር በመጋፈጥ ገቢ ጭፍራ ነው (ይባላሉ)። ለእነርሱ አይስፋቸው፤ እነርሱ እሳትን ገቢዎች ናቸውና (ይላሉ)።

قَالُوا۟ بَلْ أَنتُمْ لَا مَرْحَبًۢا بِكُمْ ۖ أَنتُمْ قَدَّمْتُمُوهُ لَنَا ۖ فَبِئْسَ ٱلْقَرَارُ ﴿٦٠﴾ قَالُوا۟ رَبَّنَا مَن قَدَّمَ لَنَا هَٰذَا فَزِدْهُ عَذَابًا ضِعْفًا فِى ٱلنَّارِ ﴿٦١﴾ وَقَالُوا۟ مَا لَنَا لَا نَرَىٰ رِجَالًا كُنَّا نَعُدُّهُم مِّنَ ٱلْأَشْرَارِ ﴿٦٢﴾ أَتَّخَذْنَٰهُمْ سِخْرِيًّا أَمْ زَاغَتْ عَنْهُمُ ٱلْأَبْصَٰرُ ﴿٦٣﴾ إِنَّ ذَٰلِكَ لَحَقٌّ تَخَاصُمُ أَهْلِ ٱلنَّارِ ﴿٦٤﴾

**60-64.** ተከታዮቹ ይላሉ፡- ይልቁን እናንተ አይስፋችሁ እናንተ ከህደቱን ለእኛ አቀረባችሁት መርጊያይቱም ገሀነም ከፋች። ጌታችን ሆይ! ይህንን ያቀረበልንን ሰው በእሳት ውስጥ እጥፍን ቅጣት ጨምርለት ይላሉ። ይላሉም ለእኛ ምን አለን? ከመጥፎዎች እንቆጥራቸው ከነበሩት ሰዎች እዚህ አናይምሳ። መቀለጃ አድርገን ያዝናቸውን? ወይስ ዓይኖቻችን ከእነርሱ ዋለሉ? ይህ በእርግጥ እውነት ነው። እርሱም የእሳት ሰዎች የእርስ በርስ የመካሰስ ወሬ ነው።

قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ مُنذِرٌ ۖ وَمَا مِنْ إِلَٰهٍ إِلَّا ٱللَّهُ ٱلْوَٰحِدُ ٱلْقَهَّارُ ﴿٦٥﴾ رَبُّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَمَا بَيْنَهُمَا ٱلْعَزِيزُ ٱلْغَفَّٰرُ ﴿٦٦﴾

**65-66.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ አስፈራሪ ብቻ ነኝ ኃያልና አንድ ከሆነ አላህ በስተቀር ምንም አምላክ የለም በላቸው። የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታ አሸናፊና መሐሪ ነው።

قُلْ هُوَ نَبَؤٌا۟ عَظِيمٌ ﴿٦٧﴾ أَنتُمْ عَنْهُ مُعْرِضُونَ ﴿٦٨﴾ مَا كَانَ لِىَ مِنْ عِلْمٍۭ بِٱلْمَلَإِ ٱلْأَعْلَىٰٓ إِذْ
يَخْتَصِمُونَ ﴿٦٩﴾ إِن يُوحَىٰٓ إِلَىَّ إِلَّآ أَنَّمَآ أَنَا۠ نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٧٠﴾

**67-70.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቁርኣን ታላቅ ዜና ነው፡፡ እናንተ ከእርሱ ዞንጊዎች ናችሁ በላቸው፡፡ በአደም ነገር በሚከራከሩህ ጊዜ በላይኛዋ ሰራዊት ለእኔ ምንም እውቀት አልነበረኝም፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እኔም አስፈሪ ገላጭ መሆኔ እንጂ ሌላ አይወርድልኝም በል፡፡

إِذْ قَالَ رَبُّكَ لِلْمَلَٰٓئِكَةِ إِنِّى خَٰلِقٌۢ بَشَرًا مِّن طِينٍ ﴿٧١﴾ فَإِذَا سَوَّيْتُهُۥ وَنَفَخْتُ فِيهِ مِن
رُّوحِى فَقَعُوا۟ لَهُۥ سَٰجِدِينَ ﴿٧٢﴾ فَسَجَدَ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ كُلُّهُمْ أَجْمَعُونَ ﴿٧٣﴾ إِلَّآ إِبْلِيسَ ٱسْتَكْبَرَ
وَكَانَ مِنَ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٧٤﴾

**71-74.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ ለመላዕክት እኔ ሰውን ከጭቃ ፈጣሪ ነኝ ባለ ጊዜ (የነበረዉን አስታውስ)፡፡ ፍጥረቱንም ባስተካከልኩና ከመንፈሴ በነፋሁበት ጊዜ ለእርሱ ሰጋጆች ሆናችሁ ውደቁ አልኩ፡፡ መላዕክትም መላውም በአንድነት ሰገዱ፡፡ ኢብሊስ ብቻ ሲቀር፡፡ ኮራ ከከሓዲያንም ነበር፡፡

قَالَ يَٰٓإِبْلِيسُ مَا مَنَعَكَ أَن تَسْجُدَ لِمَا خَلَقْتُ بِيَدَىَّ ۖ أَسْتَكْبَرْتَ أَمْ كُنتَ مِنَ
ٱلْعَالِينَ ﴿٧٥﴾ قَالَ أَنَا۠ خَيْرٌ مِّنْهُ خَلَقْتَنِى مِن نَّارٍ وَخَلَقْتَهُۥ مِن طِينٍ ﴿٧٦﴾ قَالَ فَٱخْرُجْ
مِنْهَا فَإِنَّكَ رَجِيمٌ ﴿٧٧﴾ وَإِنَّ عَلَيْكَ لَعْنَتِىٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٧٨﴾ قَالَ رَبِّ فَأَنظِرْنِىٓ إِلَىٰ يَوْمِ
يُبْعَثُونَ ﴿٧٩﴾ قَالَ فَإِنَّكَ مِنَ ٱلْمُنظَرِينَ ﴿٨٠﴾ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْوَقْتِ ٱلْمَعْلُومِ ﴿٨١﴾ قَالَ فَبِعِزَّتِكَ
لَأُغْوِيَنَّهُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٨٢﴾ إِلَّا عِبَادَكَ مِنْهُمُ ٱلْمُخْلَصِينَ ﴿٨٣﴾ قَالَ فَٱلْحَقُّ وَٱلْحَقَّ أَقُولُ ﴿٨٤﴾
لَأَمْلَأَنَّ جَهَنَّمَ مِنكَ وَمِمَّن تَبِعَكَ مِنْهُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٨٥﴾

**75-85.** አላህ ኢብሊስ ሆይ፣ በሁለት እጆቼ ለፈጠርኩት ለአደም ከመስገድ ምን ከለከለህ? (አሁን) ኮርተህ ነው ወይስ (ፊቱኑ) ከትዕቢተኞች ነበርክ አለው፡፡ (ኢብሊስም) እኔ ከእርሱ በላጭ ነኝ፡፡ እኔን ከእሳት የፈጠርከኝ ስትሆን፡፡ እሱን ግን ከጭቃ ነው የፈጠርከው አለ፡፡ አላህ፡- ከእርሷ ውጣ አንተ የተባረርክ ነህና፡፡ እርግማኔም እስከ ፍርዱ ቀን ድረስ በአንተ ላይ ይሁን አለው፡፡ ኢብሊስም ጌታየ ሆይ፣ እስከሚቀሰቀሱበት ቀን ድረስ እባክህ አቆየኝ አለ፡፡ አላህም፡- አንተ እስከ ታወቀው ወቅት ቀን ድረስ ከሚቆዩት ነህ

አለው፡፡ እርሱም አላህ በአሸናፊነትህ ይሁንብኝ ሁላቸዉንም አሳስታቸዋለሁ፡፡ ከእነርሱም ውስጥ ከተከተሉህ ባንድ ላይ ገሀነምን በእርግጥ እከታለሁ አለ፡፡ አላህ እውነቱም ከእኔ ብቻ ነው፡፡ እውነትንም እላለሁ፡፡ አንተንና ከእነርሱ ውስጥ ከተከተለህ ባንድ ላይ ገሀነምን በእርግጥ እሞላታለሁ አለው፡፡

قُلْ مَآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ مِنْ أَجْرٍ وَمَآ أَنَا۠ مِنَ ٱلْمُتَكَلِّفِينَ ﴿٨٦﴾ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿٨٧﴾
وَلَتَعْلَمُنَّ نَبَأَهُۥ بَعْدَ حِينٍۭ ﴿٨٨﴾

**86-88.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርሱ ላይ ምንም ዋጋ አል ጠይቃችሁም፡፡ እኔም ከተግደርዳሪዎች አይደለሁም በላቸው፡፡ ቁርኣን ለዓለማት መገሰጫ እንጂ ሌላ አይደለም በላቸው፡፡ የትንቢቱን እውነትነት ከጊዜ በኋላም ቢሆን በእርግጥ ታውቁታላችሁ በላቸው፡፡

**ከሷድ ምዕራፉ ከአንቀፅ (26-88) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በፍትህ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ስለ መሆኑ፤
2. ስሜትን መከተል ተገቢ ስላለ መሆኑ፤
3. የሙቶ መነሳት ሀቅነት ማሳወቅ፤
4. ይህ ዓለም ለቀልድ ነው የተፈጠረችው የሚሉ ሰዎችን ማውገዝ፤
5. አላህ ከቀልድና ከጨዋታ የፀዳ ስለመሆኑ፤
6. አዕምሮን በአግባቡ የተጠቀመ የሚያገኘው ጥቅም፤
7. ቁርኣን ያለው ረድኤትና በረከት
8. መልካም ልጅ አላህ የሰጠው ሰው አላህን ማመስገን እንደሚገባው፤
9. ስህተት ላይ እንደወደቀ ወዲው ይቅርታን የሚጠይቅ ባሪያ አላህ ዘንድ የተሰጠው ውዳሴ፤
10. አዛዦች ኃይላቸውን ለማወቅ የሚያስችላቸውን ነገሮች መጠቀም እንደሚችሉ፤
11. ከወንጀል ትልቅም ሁነ ትንሽ ይቅርታ መጠየቅ አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
12. ወደ አላህ በመልካም ስሞቹ መወሰል ወይም መለመን እንደሚገባ፤
13. አላህ ለባሪያው ለሱለይማን የዋለውን ውለታ፤
14. የነብዩን (ﷺ) ነብይት ማረጋገጥ፤
15. አላህ ከባሮቹ የሚወዳቸውን እንደሚፈትን፤
16. ትዕግስት ማድረግና በዱንያም ሆነ በአኼራ የሚያስከትለው መልካም ውጤት፤
17. አዋቂ ለሆኑ ሰዎች የጥያቄዎችን መልስ መስጠት ተገቢ ስለ መሆኑ፤
18. ማህላውን ያፈረሰ ሰው ከፋራ እንደሚወጅበበት በፍትህ ውሳኔ መስጠት ተገቢ መሆኑን፤
19. ስሜትን መከተል ተገቢ ስላለ መሆኑ፤
20. የሙቶ መነሳት ሀቅነት ማሳወቅ፤
21. በያን ላይ እውቀትና ጥንካሬ ያለው ሰው ትልቅነት፤
22. የመጨረሻዋ ዓለም ያላት ትልቅነት፤

23. አላህን መፍራት ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ፤
24. የአኼራ ፀጋዎች የማያልቁ መሆኑ፤
25. በመልካም ስራዎች አርአያ መከተል ምን ያህል ትልቅ ነገር እንደሆነ፤
26. ድንበር ማላፍን ማውገዝና በትንሳኤ ዕለት ምንዳው ምን እንደሚሆን፤
27. በእሳት ሰዎች መካከል የሚያደርጉትን ክርክሮች ማስታወስ፤
28. በትንሳኤ ዕለት ባዕድ አማልክቶችን ሲከተሉ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ለዚህ ጥፋት የመሯቸውን አለቆች አላህ እጥፍ ድርብ እንዲቀጣላቸው እንደሚጠይቁ፤
29. የእሳት ሰዎች ኋላ ቀሮች ናቸው በሚል ይንቋቸው የነበሩትን ድሀ ሙስሊሞችን ማስታወሳቸው
30. የነብዩን (ﷺ) ነብይት ማረጋገጥ፤
31. ኢብሊስ ለአደም ያለውን ጠላትነት መግለፅና ለዚህም ያበቃው ምክንያት ምቀኝትና ኩራት መሆኑ፤
32. በማነፃፀር መናገር ኢብሊስን እንደጣለው ሁሉ ስህተት ላይ ሊጥል እንደሚችል በፍትህ ውሳኔ መስጠት ተገቢ ስለ መሆኑ፤ ስሜትን መከተል ተገቢ ስላለ መሆኑ፤
33. አላህ መልካም ሰሪዎችንና እድለኞች እንደሆኑ የፃፋቸው ሰዎች ሰይጣን ሊያጠማቸውና ሊያሳስታቸው እንደማይችል፤
34. ማንም ሰው እውነትን በመናገርና ሀቅን በማብራራት ላይ ክፍያ ከፈለኝ ማለት እንደሌለበት፤
35. ለውሸት የሚያበቁ ችግሮች ውስጥ መግባት ክልክል ስለመሆኑ፤
36. ያለበት ቦታ ለዲኑ ያልተመቸው ሰው ሁሉ መሰደድ እንዳለበት፤
37. ቁርኣን የተናገራቸው ትንቢቶች በየጊዜው ተፈፃሚ መሆናቸውን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የሷድ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (39) የጭፍራዎች ምዕራፍ (ሱረቱ አዝዙመር)

سُورَةُ الزُّمَرِ

## በመካ የወረደ ምዕራፍ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (75) ናቸው።
## የሱረቱ አዝ-ዙመር መግቢያ

ምዕራፉ እንደ መካ ምእራፎች ሁሉ ስለ ቁርኣን ታላቅነት መደጋገምና የአላህን አንድነትና ብቸኛ አምላክነት የሺርክን አስከፊነት በመተንተን ነው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

تَنزِيلُ ٱلۡكِتَٰبِ مِنَ ٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَكِيمِ ١

**1.** የመጽሐፉ መወረድ አሸናፊና ጥበበኛ ከሆነው ከአላህ ነው።

إِنَّآ أَنزَلۡنَآ إِلَيۡكَ ٱلۡكِتَٰبَ بِٱلۡحَقِّ فَٱعۡبُدِ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ٢ أَلَا لِلَّهِ ٱلدِّينُ ٱلۡخَالِصُۚ
وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ مَا نَعۡبُدُهُمۡ إِلَّا لِيُقَرِّبُونَآ إِلَى ٱللَّهِ زُلۡفَىٰٓ إِنَّ ٱللَّهَ يَحۡكُمُ
بَيۡنَهُمۡ فِي مَا هُمۡ فِيهِ يَخۡتَلِفُونَۗ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي مَنۡ هُوَ كَٰذِبٞ كَفَّارٞ ٣

**2-3.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ወደ አንተ መጽሐፉን በእውነት የተሞላ ሲሆን አወረድነው። አላህንም ሃይማኖትን ለእርሱ ብቻ ያጠራህ ሆነህ ተገዛው። (ሙስሊሞች ሆይ!) አስተውሉ ፍፁም ጥሩ የሆነው ሃይማኖት ለአላህ ብቻ ነው። እነዚያ ከእርሱ ሌላ ጣዖታትን ረዳቶች አድርገው የያዙት ሰዎች ሁሉ ወደ አላህ ማቃረብን እንዲያቃርቡን እንጂ ለሌላ አንገዛቸውም ይላሉ። አላህ በዚያ እነርሱ በእነርሱ በሚለያዩበት ነገር በመካከላቸው ይፈርዳል። አላህ እርሱ ውሸታምንና ከሓዲ የሆነን ሰው አያቀናም።

ከጭፍራዎች ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አሚር፤ ጊናና በኒሰሊም የተባሉ ሶስት ብሄሮች ጣኦት ያመልኩ የነበሩና መላኢኮች የአላህ ሴት ልጆች ናቸው ይሉ የነበሩትን ሰዎች ለማስተማር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

لَّوۡ أَرَادَ ٱللَّهُ أَن يَتَّخِذَ وَلَدٗا لَّٱصۡطَفَىٰ مِمَّا يَخۡلُقُ مَا يَشَآءُۚ سُبۡحَٰنَهُۥۖ هُوَ ٱللَّهُ ٱلۡوَٰحِدُ ٱلۡقَهَّارُ ٤

4. አላህ ልጅን መያዝ በፈለገ ኖሮ ከሚፈጥረው ውስጥ የሚሻውን ይመርጥ ነበር። ጥራት ተገባው። እርሱ አሸናፊውና ብቸኛው አንዱ አላህ ነው።

خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّۖ يُكَوِّرُ ٱلَّيۡلَ عَلَى ٱلنَّهَارِ وَيُكَوِّرُ ٱلنَّهَارَ عَلَى ٱلَّيۡلِۖ وَسَخَّرَ
ٱلشَّمۡسَ وَٱلۡقَمَرَۖ كُلّٞ يَجۡرِي لِأَجَلٖ مُّسَمًّىۗ أَلَا هُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡغَفَّٰرُ ٥

5. አላህ ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ። ሌሊትንም በቀን ላይ ይጠቀልላል። ቀንንም በሌሊት ላይ እንዲሁ ይጠቀልላል። ፀሐይንና ጨረቃንም ገራ። ሁሉም ለተወሰነ ጊዜ ይሮጣሉ። ሙስሊሞች ሆይ! አስተውሉ! እርሱ አሸናፊና መሀሪ ነውና።

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፦**

1. የነብዩን (ﷺ) ነብይት ማረጋገጥ፤
2. ተውሒድን ማፅደቅና ሽርክን ማውገዝ፤
3. ሙቶ መነሳትንና የቂያማ ቀንን ማረጋገጥ እንማራለን።

خَلَقَكُم مِّن نَّفۡسٖ وَٰحِدَةٖ ثُمَّ جَعَلَ مِنۡهَا زَوۡجَهَا وَأَنزَلَ لَكُم مِّنَ ٱلۡأَنۡعَٰمِ ثَمَٰنِيَةَ أَزۡوَٰجٖۚ
يَخۡلُقُكُمۡ فِي بُطُونِ أُمَّهَٰتِكُمۡ خَلۡقٗا مِّنۢ بَعۡدِ خَلۡقٖ فِي ظُلُمَٰتٖ ثَلَٰثٖۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمۡ
لَهُ ٱلۡمُلۡكُۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ فَأَنَّىٰ تُصۡرَفُونَ ٦

6. (ሰዎች ሆይ)፣ ከአንዲት ነፍስ ፈጠራችሁ። ከዚያ ከእርሷ መቀናጀዋን ፈጠረ። ለእናንተም ከግመልና ከዳልጋ ከብት፤ ከፍየልና ከበግ ስምንት አይነቶችን ወንድና ሴት አወረደ*። በእናቶቻችሁ ሆዶች ውስጥ በሶስት ጨለማዎች ውስጥ ከመፍጠር በኋላ ሙሉ መፍጠርን ይፈጥራችኋል፤ ይህን ያደረገው ጌታችሁ አላህ ነው። ስልጣኑም የእርሱ ብቻ ነው። ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ አምላክ የለም። ታዲያ ወዴት ትዞራላችሁ።

* አወረደ፡- ፈጠረ፤ ገራ፤ ወሰነ፤ የእንስሳትም ህይወት በዝናብ ምክኒያት ስለሆነም ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት መአል አዕራፍ ም. ከ (143) እና (144) ኛው አንቀፅላይ የተዘረዘሩትን ማለት ነው።

إِن تَكۡفُرُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَنِيٌّ عَنكُمۡۖ وَلَا يَرۡضَىٰ لِعِبَادِهِ ٱلۡكُفۡرَۖ وَإِن تَشۡكُرُواْ يَرۡضَهُ لَكُمۡۗ
وَلَا تَزِرُ وَازِرَةٞ وِزۡرَ أُخۡرَىٰۚ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُم مَّرۡجِعُكُمۡ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَۚ إِنَّهُۥ
عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٧

7. (ሰዎች ሆይ)፣ በአላህ ብትክዱ አላህ ከናንተ የተብቃቃ ነው። ለባሪያዎቹም ክህደትን አይወድም፤ ብታመሰግኑ እርሱ ይወድላችኋል። ማንኛይቱም ኃጢአትን ተሸካሚ ነፍስ የሌላይቱን ኃጢአት አትሸከምም፤ ከዚያ የሁላችሁም መመለሻችሁ ወደ ጌታችሁ ብቻ ነው፤ ትሰሩት የነበራችሁንም ሁሉ ይንግራችኋል፤ እርሱ በልቦች ውስጥ ያሉትን ሁሉ አዋቂ ነውና።

۞وَإِذَا مَسَّ ٱلۡإِنسَٰنَ ضُرّٞ دَعَا رَبَّهُۥ مُنِيبًا إِلَيۡهِ ثُمَّ إِذَا خَوَّلَهُۥ نِعۡمَةٗ مِّنۡهُ نَسِيَ مَا كَانَ يَدۡعُوٓاْ
إِلَيۡهِ مِن قَبۡلُ وَجَعَلَ لِلَّهِ أَندَادٗا لِّيُضِلَّ عَن سَبِيلِهِۦۚ قُلۡ تَمَتَّعۡ بِكُفۡرِكَ قَلِيلًا إِنَّكَ مِنۡ
أَصۡحَٰبِ ٱلنَّارِ ٨

8. የሰውን ልጅ ጉዳት ባገኘው ጊዜ ጌታውን ወደ እርሱ ተመላሽ ሆኖ ይጠራል። ከዚያ ከእርሱ ዘንድ ፀጋን በሰጠው ጊዜ ያንን ከዚያ በፊት ወደ እርሱ ይፀልይበት የነበረውን መከራ ይረሳል፤ ከመንገዱ ለማሳሳትም ለአላህ ባላንጣዎችን ያደርጋል። ለእንዲህ አይነቱ ሰው በክህደት ጥቂትን ተጣቀም፤ አንተ በእርግጥ ከእሳት ጓዶች ነህ በለው።

ከጭፍራዎች ምዕራፍ (8) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዑስማን ኢቢኑ አፋን ወይም በአማር ኢብኑ ያሲር ወይም በዐብዱላህ ኢኢብኑ መስዑድ ምክንያት ነው የወረደው ይላሉ። (ሱዩጢ።)

أَمَّنۡ هُوَ قَٰنِتٌ ءَانَآءَ ٱلَّيۡلِ سَاجِدٗا وَقَآئِمٗا يَحۡذَرُ ٱلۡأٓخِرَةَ وَيَرۡجُواْ رَحۡمَةَ رَبِّهِۦۗ قُلۡ هَلۡ
يَسۡتَوِي ٱلَّذِينَ يَعۡلَمُونَ وَٱلَّذِينَ لَا يَعۡلَمُونَۗ إِنَّمَا يَتَذَكَّرُ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٩

9. ያ የመጨረሻይቱን ዓለም ቅጣት የሚፈራ የጌታውንም ችሮታ የሚከጅል ሲሆን በሌሊት ሰዓቶችም ሰጋጅና ቋሚ ሆኖ ለጌታው የሚገዛ ሰው እንደ ተስፋ ቢሱ ከሓዲ ነውን? በለው። እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይስተካከላሉን? በላቸው። የሚገነዘቡት ባለ አእምሮዎች ብቻ ናቸው።

قُلۡ يَٰعِبَادِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ رَبَّكُمۡۚ لِلَّذِينَ أَحۡسَنُواْ فِي هَٰذِهِ ٱلدُّنۡيَا حَسَنَةٞۗ وَأَرۡضُ ٱللَّهِ
وَٰسِعَةٌۗ إِنَّمَا يُوَفَّى ٱلصَّٰبِرُونَ أَجۡرَهُم بِغَيۡرِ حِسَابٖ ١٠

10. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ጌታችሁ) እናንተ ያመናችሁ ባሮቼ ሆይ! ጌታችሁን ፍሩ። ለእነዚያ በዚህች በቅርቢቱ ዓለም መልካም ለሰሩት መልካም ምንዳ አላቸው። የአላህ ምድርም ሰፊ ናት፤ ብትቸገሩም ተሰደዱ። ታጋሾች ምንዳቸውን የሚሰጡት ያለ ግምት ነው።[*1] ይላል በላቸው።[*2]

✶1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተከታዩን ሲናገሩ አድምጫለሁ በማለት አነስ አስተላልፈዋል፦ «አላህ ባሪያዬን በሁለት በሚወዳቸው (አይኖቹ) ላይ ፈተና አድርሸበት ትዕግስት ካደረገ የምሰጠው ለውጥ ጀነትን ነው» ብሏል። «ሁለት ወዳጆች» የሚለው ቃል የሚያመለክተው ሁለቱን ዓይኖቹን ነው።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ዐብደላህ ኸባብ ኢብኑ አል. አረት እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ከካዕባ ጥላ ስር ብቻቸውን ተንተርሰው ሳሉ፦ «ከአላህ ዘንድ ድልን አይለምኑልንም? ዱዓስ አያደርጉልንም? በማለት ስሞታ አቀረኢብኑላቸው። «ከናንተ በፊት በነበረው ዘመን ሰውየው ይያዝና ጉድጓድ ተቆፍሮ በውስጡ እንዲገባ ይደረጋል። መጋዝ ይቀርብና ከራሱ ላይ ተደርጎ ከሁለቱ ይሰነጠቃል። ስጋውን ዘልቆ አጥንቱን ድረስ በሚገባ የብረት ሚዶ ይላጋል። ይህ ሁኔታ ከዲኑ አያስተጓጉለውም። በአላህ ይሁንብኝ! አላህ ይህን ጉዳይ ይሞላዋል። አንድ ተጓዥ ከሰንዓ እስከ ሐድረመውት ከአላህ ውጭ ምንንም የማይፈራ ሆኖ መጓዝ እስኪችል ድረስ ሌላው ቀርቶ ተኩላ ፍየሎችን ይተነኩልብኛል የሚል ስጋት ሳያድርበት ግና እናተ ትቸኩላላችሁ።»

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላለፉት፦ የሁነይን ዘመቻ ዕለት ነበር። የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በምርኮ አከፋፈል ላይ ለተወሰኑ ሰዎች ከሌሎች ብልጫ ያለው ድርሻ ሰጡ። ለአረዕ ኢብኑ ሐቢብ መቶ ግመሎችን ለሀሱ። ለዐየነህ ኢብኑ ሒሰንም እንዲሁ። ከዐረብ ታላላቅ ሰዎች ለተወሰኑትም ድርሻቸውን ሰጡ። በጊዜው ከሌሎች ብልጫ ያለው ድርሻ ነበር የሰጧቸው። «በእውነቱ ይህ ክፍፍል ፍትህ የጎደለውና የአላህ ውዴታ ያልተከጀለበት ክፍፍል ነው» ሲል አንድ ሰው ተናገረ። «በአላህ ይሁንብኝ ይህንን ቃልህን ለአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እነግራቸዋለሁ» አልኩት። እርሳቸው ዘንድ በመቅረብ ያለውን ነገርኳቸው። ፊታቸው ተለዋወጠ። ፍም መሰለ። «አላህና መልዕክተኛው ፍትሃዊ ካልሆኑ ማን ነው ፍትሃዊ ሊሆን የሚችለው?» ካሉ በኋላ «ለሙሳ አላህ ይዘንለት። ከዚህ ይበልጥ መከራ ደርሶበት በትዕግስት አሳልፎታል» አሉ። ከእንግዲህ እንዲህ አይነቱን ወሬ አላደርስላቸውም አልኩ።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሃዲስ አነስ እንዲህ ሲሉ አስተላፈዋል፦ አቡ ጦልሐ ህመም የሚያጣድፈው ልጅ ነበራቸው። ለጉዞው ሲወጡ ህፃኑ ልጃቸው ሞተ። ከጉዞ ተመለሱና፦ «ልጁን ምን አገኘው?» ሲሉ ጠየቁ። ኡሙ ሱለይም የሕፃኑ እናት «ከበፊቱ በረድ ብሎለታል» ስትል መለሰች። ራት አቀረበችላቸው። ተመገቡ። ግብረ. ስጋ ግንኙነት ፈፅመው ሲያጠናቅቁ «ህፃኑን ይቅበሩት» አለቻቸው። ሲነጋ ከአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በመቅረብ የሆነውን አጫወቷቸው አቡ ጦልሐ «ግብረ. ስጋ ግንኙነት ፈፀማችሁን?» ሲሉ መልዕክተኛ ጠየቁ። «አዎ!» አቡ ጦልሐ መለሱ። «አላህ ሆይ! ባርክላቸው» ሲሉ መልዕክተኛው (ﷺ) ዱዓ አደረጉ። ወንድ ልጅ ወለደች። ከነብዩ ዘንድም ውሰደው አሉኝ አቡ ጦልሐ ተምሮችንም አብረው ላኩ። «ከርሱ ጋር የመጣ ነገር አለ? ሲሉ መልዕክተኛው (ﷺ) ጠየቁ። «አዎ» ተምሮች አሉ» የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) አንዷን ተምር ያዙና አላመጧት። ከአፋቸው አወጡና ከህፃኑ አፍ ውስጥ ከተቱት። የአፉን ውስጥም በተምሯ ፈገፈጉት። ዐብደላህ ብለው ሰየሙት።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፦ «ኃይል ማለት ተፎካካሪዎቹን ታግሎ የሚያሸንፍ ሳይሆን በቁጣ ወቅት ራሱን መቆጣጠር የሚችል ነው።»

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ እንዲህ ሲሉ አስተላፈዋል፦ ዑየይነህ ኢብኑ ሒስን ወደ መዲና በመምጣት ከወንድሙ ልጅ ከሑር ኢብኑ ቀይስ ዘንድ አረፈ። ሑር ዑመር ከሚያቀርባቸው ሰዎች አንዱ ነበር። የቁርአንን መልዕክት የመረዳት የላቀ ችሎታ ያላቸው ሰዎች ወጣቶችም ይሁኑ ሽማግሌዎች የኡመር ችሎት አባላትና አማካሪዎችም ነበሩ። «የወንድሜ ልጅ ሆይ! በዚህ አዛኝ መሪ ዘንድ ተደማጭነት ያለህ ሰው ነህና ከፊቱ መቅረብ እችል ዘንድ ፈቃድ ጠይቅልኝ» በማለት ዑየይነህ የወንድሙን ልጅ ይጤቃል። ፈቃድ ጠየቀለት። ዑመር ፈቀዱለት ዑመር ዘንድ በቀረበ ጊዜ «በአላህ እምላለሁ! የኸጣብ ልጅ! በርከት ያለ ስጦታ አትስጠንም፤ በፍትህ አትፈርድልንም» በማለት ተናገረ።

ዑመር አለቅጥ ተቆጡ። ሊቀጡት እስኪከጅሉ ድረስ። ሑር እንዲህ አላቸው፡- «የሚእሚኖች አሚር ሆይ! አላህ ለነብዩ (ﷺ) «ገር ጠባይ ያዝ፤ በመልካም እዘዝ፤ ባለጌዎችን ተዋቸው» ብሏል። ይህ ሰው ደግሞ ከባለጌዎች አንዱ ነው።» ሑር ይህንን የቁርኣን አንቀፅ ባነበበት ወቅት ዑመር ቁታቸው በረደ። ዑመር የአላህን መመሪያ ቅንጣት የማይተላለፉ ነበሩ።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጠላትን ለመግጠም ከወጡባቸው ቀናት በአንዷ ፀሐይ ወደ ምዕራብ ዘንበል እስከትል ድረስ ከጠበቀ በኋላ ከሰዎች መካከል በመቆም «እናተ ሰዎች ሆይ! ከጠላት መግጠምን አትመኙ፤ አላህን ሰላምን ለምኑት። ከገጠማችኋቸው ደግሞ ትዕግስትና ፅናት ይኑራችሁ። ጀነት ከሾተል ጥላ ስር መሆኑንም እወቁ።» ካሉ በኋላ «ኪታኢብኑ ያወረድክ፤ ዳመናን የምትነዳ፤ የከሓዲያንን ጥርቅም አሸናፊ የሆንከው አላህ ሆይ! አሸንፋቸው፤ በነርሱ ላይ ድልን አቀዳጀን።» ሲሉ አላህን ተማፀኑ።

✷2 በጃዕፋር ኢብኑ አቡ ጧሊብ መሪነት ወደ ሐበሻ መምጣት ባሰቡበት ጊዜ የወረደ አንቀፅ እንደሆነ ይነገራል።

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (6-10) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ በዚህች ዓለም ላይ ያስቀመጣቸው ተዓምሮችን በመመልከት ተውሒድን እንድንማር ማድረግ፤
2. አላህ ባሮቹን በመፍጠርና በመመገብ የዋለውን ውለታ ማስታወስ፤
3. ክህደት ከእምነት የበለጠና ለማመን ብዙ ማስረጃዎችን ማምጣት ሲቻል ለመካድ ግን አንድም አለመኖሩን፤
4. አላህ ከፍጡሩ የተብቃቃና ፍጡሮቹ ሁሉ ወደ እርሱ ፈላጊ ስለመሆናቸው፤
5. አላህ የቂያማ ዕለት በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ፍትሃዊ መሆኑ፤
6. አላህ ሁሉን ነገር የሚያውቅ ስለመሆኑ እንማራለን።

قُلۡ إِنِّيٓ أُمِرۡتُ أَنۡ أَعۡبُدَ ٱللَّهَ مُخۡلِصٗا لَّهُ ٱلدِّينَ ١١ وَأُمِرۡتُ لِأَنۡ أَكُونَ أَوَّلَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ١٢

**11-12.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ አላህን ሃይማኖትን ለእርሱ ያጠራሁ ሆኜ እንድገዛው ታዘዝኩ። የሙስሊሞች መጀመሪያ እንድሆን ታዘዝኩ በል።

قُلۡ إِنِّيٓ أَخَافُ إِنۡ عَصَيۡتُ رَبِّي عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ١٣ قُلِ ٱللَّهَ أَعۡبُدُ مُخۡلِصٗا لَّهُۥ دِينِي ١٤

**13-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ ከጌታዬ ባምፅ የታላቁን ቀን ቅጣት እፈራለሁ በል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህን ሃይማኖቴን ለእርሱ ያጠራሁ ሆኜ እገዛዋለሁ በል።

فَٱعۡبُدُواْ مَا شِئۡتُم مِّن دُونِهِۦۗ قُلۡ إِنَّ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ وَأَهۡلِيهِمۡ يَوۡمَ
ٱلۡقِيَٰمَةِۗ أَلَا ذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡخُسۡرَانُ ٱلۡمُبِينُ ١٥ لَهُم مِّن فَوۡقِهِمۡ ظُلَلٞ مِّنَ ٱلنَّارِ وَمِن تَحۡتِهِمۡ
ظُلَلٞۚ ذَٰلِكَ يُخَوِّفُ ٱللَّهُ بِهِۦ عِبَادَهُۥۚ يَٰعِبَادِ فَٱتَّقُونِ ١٦

**15-16.** ከእርሱ ሌላ የሻችሁትን ተገዙ ከሳሪዎች ማለት እነዚያ በትንሳኤ ቀን ነፍሶቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን ያከሰሩ ናቸው። ሰዎች ሆይ ንቁ ግልፅ ከሳራ ማለት ይህ ነው በላቸው። ለእነርሱ ከበላያቸው ከእሳት የሆኑ ድርብርብ ጥላዎች አሏቸው። ከስራቸዉም እንዲሁ። ይህ አላህ ባሮቹን እንዲጠነቀቁ በእርሱ ያስፈራራበታል። ባሮቼ ሆይ! ስለዚህ ፍሩኝ።

وَٱلَّذِينَ ٱجۡتَنَبُواْ ٱلطَّٰغُوتَ أَن يَعۡبُدُوهَا وَأَنَابُوٓاْ إِلَى ٱللَّهِ لَهُمُ ٱلۡبُشۡرَىٰۚ فَبَشِّرۡ عِبَادِ ﴿١٧﴾ ٱلَّذِينَ يَسۡتَمِعُونَ ٱلۡقَوۡلَ فَيَتَّبِعُونَ أَحۡسَنَهُۥٓۚ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ هَدَىٰهُمُ ٱللَّهُۖ وَأُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ أُوْلُواْ ٱلۡأَلۡبَٰبِ ﴿١٨﴾

**17-18.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያም ጣዖታትን ከመገዛት የራቁ እና ወደ አላህ የዞሩ ሁሉ ለእነርሱ ታላቅ ብስራት አላቸው። ስለዚህ ባሮቸን አብስር። እነዚያን ንግግርን የሚያዳምጡትንና መልካምን የሚከተሉትን (አብስር)፤ እነዚያ አላህ ወደ ቀናው መንገድ የመራቸው ናቸው። እነዚያም እነርሱ ባለ አእምሮዎቹ ናቸው።

أَفَمَنۡ حَقَّ عَلَيۡهِ كَلِمَةُ ٱلۡعَذَابِ أَفَأَنتَ تُنقِذُ مَن فِي ٱلنَّارِ ﴿١٩﴾ لَٰكِنِ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوۡاْ رَبَّهُمۡ لَهُمۡ غُرَفٞ مِّن فَوۡقِهَا غُرَفٞ مَّبۡنِيَّةٞ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۖ وَعۡدَ ٱللَّهِ لَا يُخۡلِفُ ٱللَّهُ ٱلۡمِيعَادَ ﴿٢٠﴾

**19-20.** በእርሱ ላይ የቅጣት ቃል የተረጋገጠችበት ሰው ትመራዋለህን? አንተ በእሳት ውስጥ ያለን ሰው ታድናለህን? ግን እነዚያ ጌታቸውን የፈሩ፤ ለእነርሱም ከበላያቸው የታነፁ ሰገነቶች የሏቸው ሰገነቶች ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን የሆኑ አሏቸው። (ይህንን) አላህ ቃል ገባላቸው፤ አላህ ቃሉን አያፈርስም።

ከጭፍራዎች ምዕራፍ (17-20) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በጃሂሊያ ጊዜ ላኢላሀ ኢለላህ የአላህን ብቸኛ አምላክነት ለመሰከሩና ሽርክን ሲቃወሙ ለነበሩት ሶስት ሰዎች ማለትም ሰኢድ ኢብኑ አምር፤ አቡዘር አልኪፋሪና ሰልማን አልፈርሲይ በተባሉት ሰዎች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሲዩጢ)

(ለ) በአቡበክር በሰለሙበት ጊዜ ኡስማን ዐብዱረህማን ጦልሐና ዙበይርን ሰዒድ ቢን ዘይንና ሰዕድ ቢን አቢ ወቃስ አቡበከርን ጠይቀው ስለ ኢማናቸው ሲነግሯቸው ስለ አመኑ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

أَلَمۡ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ أَنزَلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ فَسَلَكَهُۥ يَنَٰبِيعَ فِي ٱلۡأَرۡضِ ثُمَّ يُخۡرِجُ بِهِۦ زَرۡعٗا مُّخۡتَلِفًا أَلۡوَٰنُهُۥ ثُمَّ يَهِيجُ فَتَرَىٰهُ مُصۡفَرّٗا ثُمَّ يَجۡعَلُهُۥ حُطَٰمًاۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَذِكۡرَىٰ لِأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ﴿٢١﴾

**21.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ከሰማይ ውሃን እንዳወረደና በምድር ውስጥ ምንጮች አድርጎ እንዳስገባው አላየህምን? ከዚያ በእርሱ ብዙ አይነቶች የሆኑ የተለያዩን አዝመራዎች ያወጣል፤ ከዚያም ይደርቃል፤ ገርጥቶም ታየዋለህ ከዚያ ስብርብር ያደርገዋል፤ በዚህ ውስጥ ለባለ አእምሮዎች ግሳፄ አለበት።

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (11-21) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. አላህ መልዕክተኛውንና አማኞችን እንደሚንከባከብ፤
2. አላህን መፍራትና በእሱ ዙሪያ ለሚፈጠሩ ችግሮች ትዕግስት ማድረግ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
3. ተውሒድን በማስረጃዎች ማረጋገጥ፤
4. የኢስላምንና የሙስሊሞችን ትልቅነት መግለፅ፤
5. ሙቶ መነሳት ትክክል ስለመሆኑ ልዩ ልዩ ማስረጃዎች፤
6. በዱንያ ያሉ ኪሳራዎች ሁሉ በአኼራ ኪሳራዎች ጋር ሲነፃፀር ከምንም ክስረት ጋር እንደማይመደቡ
7. የዘይድ ኢብኑ የአቡዘር እና የሰልማነል ፋርሲይ ትልቅነት፤
8. ነገሮችን ሰምተው የሚያመዛዝኑ ሰዎች በአላህ ዘንድ ያላቸው ክብር፤
9. ትምህርት የሚወሰደው ከተገኘበት ሲሆን የአስተማሪው አቋም የግድ የተማሪውን አቋም መምሰል እንደሌለበት፤
10. በትክክል አላህን አምነው ለሚፈሩ ሰዎች በጀነት ያዘጋጀላቸውን ፀጋ በጥቂቱ እንማራለን።

أَفَمَن شَرَحَ ٱللَّهُ صَدۡرَهُۥ لِلۡإِسۡلَٰمِ فَهُوَ عَلَىٰ نُورٖ مِّن رَّبِّهِۦۚ فَوَيۡلٞ لِّلۡقَٰسِيَةِ قُلُوبُهُم مِّن ذِكۡرِ
ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٍ ﴿٢٢﴾

**22.** አላህ ደረቱን ለእስልምና ያሰፋለትና እርሱም ከጌታው ዘንድ በብርሃን ላይ የሆነ ሰው ልቡ እንደ ደረቀ ሰው ነውን? ልቦቻቸውም ከአላህ መወሳት ለደረቁ ሰዎች ወየውላቸው እነዚያ በግልፅ መሳሳት ውስጥ ናቸው።

ٱللَّهُ نَزَّلَ أَحۡسَنَ ٱلۡحَدِيثِ كِتَٰبٗا مُّتَشَٰبِهٗا مَّثَانِيَ تَقۡشَعِرُّ مِنۡهُ جُلُودُ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُمۡ
ثُمَّ تَلِينُ جُلُودُهُمۡ وَقُلُوبُهُمۡ إِلَىٰ ذِكۡرِ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ هُدَى ٱللَّهِ يَهۡدِي بِهِۦ مَن يَشَآءُۚ وَمَن
يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِنۡ هَادٍ ﴿٢٣﴾

**23.** አላህ ከዜና ሁሉ መልካምን ተመሳሳይ ተደጋጋሚ የሆነን መጽሐፍ (ቁርኣንን) አወረደ። ከእርሱ ግሳፄ የእነዚያ ጌታቸውን የሚፈሩት ሰዎች ቆዳዎች ይኮማተራሉ። ከዚያ ቆዳዎቻቸውና ልቦቻቸው ወደ አላህ ተስፋ ማስታወስ ይለዝባሉ። ይህ የአላህ መምሪያ ነው፤ በእርሱ የሚሻውን ሰው ይመራበታል አላህም የሚያጠመው ሰው ለእርሱም ምንም አቅኚ የለውም።

ከጭፍራዎች ምዕራፍ (23) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በሱረቱ ዩሱፍ መግቢያ ላይ እንዳለፈው ሁሉ ሙስሊሞች ታሪክ ቢተርኩልን ብለው ስለጠየቋቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَفَمَن يَتَّقِي بِوَجْهِهِۦ سُوٓءَ ٱلْعَذَابِ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۚ وَقِيلَ لِلظَّٰلِمِينَ ذُوقُوا۟ مَا كُنتُمْ تَكْسِبُونَ ٢٤

**24.** በትንሳኤ ቀን ክፉን ቅጣት በፊቱ የሚመክት ሰው ከቅጣት እንደሚድን ነውን? ለበዳዮችም ትሰሩት የነበራችሁን ቅጣትን ቅመሱ ይባላሉ።

كَذَّبَ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ فَأَتَىٰهُمُ ٱلْعَذَابُ مِنْ حَيْثُ لَا يَشْعُرُونَ ٢٥ فَأَذَاقَهُمُ ٱللَّهُ ٱلْخِزْىَ
فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَلَعَذَابُ ٱلْءَاخِرَةِ أَكْبَرُ ۚ لَوْ كَانُوا۟ يَعْلَمُونَ ٢٦

**25-26.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ በፊት የነበሩት አስተባበሉ፤ ቅጣትም ከማያውቁት በኩል መጣባቸው። አላህ በቅርቢቱ ሕይወት ውርደትን አቀመሳቸው። የመጨረሻይቱ ዓለም ቅጣት በጣም ትልቅ ነው። የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ አያስተባብሉም ነበር።

وَلَقَدْ ضَرَبْنَا لِلنَّاسِ فِى هَٰذَا ٱلْقُرْءَانِ مِن كُلِّ مَثَلٍ لَّعَلَّهُمْ يَتَذَكَّرُونَ ٢٧ قُرْءَانًا عَرَبِيًّا
غَيْرَ ذِى عِوَجٍ لَّعَلَّهُمْ يَتَّقُونَ ٢٨

**27-28.** በዚህም ቁርኣን ውስጥ ለሰዎች ይገሰፁ ዘንድ ከየምሳሌው ሁሉ በእርግጥ አብራራን፤ መዛባት የሌለበት አረብኛ ቁርኣን ሲሆን አብራራነው፤ ሊጠነቀቁ ይከጀላልና።

ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا رَّجُلًا فِيهِ شُرَكَآءُ مُتَشَٰكِسُونَ وَرَجُلًا سَلَمًا لِّرَجُلٍ هَلْ يَسْتَوِيَانِ مَثَلًا ۚ
ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ ۚ بَلْ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ٢٩

**29.** አላህ በእርሱ ተጨቃጫቂዎች የሆኑ ተጋሪዎች ያሉትን ባሪያና ለአንድ ሰው ብቻ ንፁህ የሆነን ባሪያ ለሚያጋራና በአንድነት ለሚያምን ሰው ምሳሌ አደረገ፤ በምሳሌ ይስተካከላሉን? ምስጋና ሁሉ ለአላህ ይገባው በእውነቱ አብዛሀኞቻቸው አያውቁም።

إِنَّكَ مَيِّتٌ وَإِنَّهُم مَّيِّتُونَ ٣٠ ثُمَّ إِنَّكُمْ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ عِندَ رَبِّكُمْ تَخْتَصِمُونَ ٣١

**30-31.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ ሟች ነህ፤ እነርሱም ሟቾች ናቸው። ከዚያ እናንተ በትንሳኤ ቀን እጌታችሁ ዘንድ ትከራከራላችሁ።

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (22-31) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን እውቀት ስፋትና ኃያልነት የሚያሳዩ ክንውኖችና ክስተቶች፤
2. አላህ ሁለት አይነት ቀልቦች ለሰዎች እንደሰጠ አንዱ በቀላሉ የአላህን ጥሪ የሚቀበል ሲሆን ሌላው ደግሞ አመፀኛ መሆኑን፤
3. ቁርኣን የሰው ልጆች በተለይም አማኞችን ከሚወያዩበት ሁሉ የተሻለ መሆኑን፤
4. አላህን መፍራት ምን ያህል ጥቅም እንዳለው፤
5. ለት ት ምሳሌዎችን መጥቀስ ተገቢ ስለመሆኑ፤
6. አጋሪና አማኝ በምን በምን እንደሚመሳሰሉ መግለፅ፤
7. ህይወት ሁሉ ሞትን እንደምትቀምስ፤
8. የትንሳኤ ዕለት ጭቅጭቆች እንደሚኖሩና አላህ ብይን እንደሚሰጥባቸው እንማራለን።

۞ فَمَنْ أَظْلَمُ مِمَّن كَذَبَ عَلَى ٱللَّهِ وَكَذَّبَ بِٱلصِّدْقِ إِذْ جَآءَهُۥٓ ۚ
أَلَيْسَ فِى جَهَنَّمَ مَثْوًى لِّلْكَٰفِرِينَ ﴿٣٢﴾

32. *በአላህ ላይም ከዋሸ እውነቱንም በመጣለት ጊዜ ከአስተባበለ ሰው ይበልጥ በዳይ ማን ነው? በገሀነም ውስጥ ለከሓዲያን መኖሪያ የለምን? (አለ እንጂ)።

✷ 24ኛው ክፍል (ጁዝ)

وَٱلَّذِى جَآءَ بِٱلصِّدْقِ وَصَدَّقَ بِهِۦٓ ۙ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُتَّقُونَ ﴿٣٣﴾ لَهُم مَّا يَشَآءُونَ عِندَ رَبِّهِمْ ۚ
ذَٰلِكَ جَزَآءُ ٱلْمُحْسِنِينَ ﴿٣٤﴾ لِيُكَفِّرَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ أَسْوَأَ ٱلَّذِى عَمِلُوا۟ وَيَجْزِيَهُمْ أَجْرَهُم
بِأَحْسَنِ ٱلَّذِى كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿٣٥﴾ أَلَيْسَ ٱللَّهُ بِكَافٍ عَبْدَهُۥ ۖ وَيُخَوِّفُونَكَ بِٱلَّذِينَ مِن
دُونِهِۦ ۚ وَمَن يُضْلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِنْ هَادٍ ﴿٣٦﴾ وَمَن يَهْدِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِن مُّضِلٍّ ۗ
أَلَيْسَ ٱللَّهُ بِعَزِيزٍ ذِى ٱنتِقَامٍ ﴿٣٧﴾

33-37. ያም በእውነት የመጣውና በእርሱ ያመነውም እነዚያ እነርሱ አላህን ፈሪዎች ናቸው። ለእነርሱም በጌታቸው ዘንድ የሚሹት (የሚፈልጉት) ሁሉ አላቸው። ይህ የበጎ አድራጊዎች ምንዳ ነው። አላህ ያንን በስህተት የሰሩትን መጥፎ ስራ ከእነርሱ ሊሰርዝላቸውና በዚያም ይሰሩት የነበሩት መልካም ስራ ምንዳቸውን ሊመነዳቸው ይህንን አደረገ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ለባሪያው በቂ አይደለምን? በእነዚያ ከእርሱ ሌላ በሆኑትም ጣኦታት ያስፈራሩሃል።፤ አላህ የሚያጠመውን ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም። አላህ የሚያቀናውን ሰው ለእርሱ ምንም አጥማሚ የለውም። አላህ አሸናፊ; የመበቀል ባለቤት አይደለምን?

وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُ ۚ قُلْ أَفَرَءَيْتُم مَّا تَدْعُونَ مِن دُونِ
ٱللَّهِ إِنْ أَرَادَنِىَ ٱللَّهُ بِضُرٍّ هَلْ هُنَّ كَٰشِفَٰتُ ضُرِّهِۦٓ أَوْ أَرَادَنِى بِرَحْمَةٍ هَلْ هُنَّ مُمْسِكَٰتُ
رَحْمَتِهِۦ ۚ قُلْ حَسْبِىَ ٱللَّهُ ۖ عَلَيْهِ يَتَوَكَّلُ ٱلْمُتَوَكِّلُونَ ﴿٣٨﴾

38. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰማያትንና ምድርን የፈጠረ ማን እንደሆነ ብትጠይቃቸው አላህ ነው ይሉሃል። ከአላህ ሌላ የምትገዟቸውን ጣዖታት አያችሁን? ንገሩኝ አላህ በጉዳት ቢፈልገኝ ለእነርሱ ጉዳትን ገላጮች ናቸውን? ወይስ በችሮታው ቢፈቅደኝ እነርሱም ችሮታውን አጋጆች ናቸውን? በላቸው። አላህ በቂዬ ነው፤ በእርሱ ላይ ተመኪዎች ይመካሉ በል።

قُلْ يَٰقَوْمِ ٱعْمَلُوا۟ عَلَىٰ مَكَانَتِكُمْ إِنِّى عَٰمِلٌ ۖ فَسَوْفَ تَعْلَمُونَ ﴿٣٩﴾
مَن يَأْتِيهِ عَذَابٌ يُخْزِيهِ وَيَحِلُّ عَلَيْهِ عَذَابٌ مُّقِيمٌ ﴿٤٠﴾

39-40. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው ህዝቦቼ ሆይ፣ ባላችሁበት ሁኔታ ላይ ሁናችሁ ስሩ። እኔም ባለሁበት ሁኔታ ላይ ሁኜ ሰሪ ነኝና። ወደ ፊትም ትክክለኛው የቱ እንደነበር ታውቃላችሁ። ያንን የሚያሳፍረው ቅጣት የሚመጣበትንና በእርሱ ላይ ዘወታሪ ቅጣት የሚሰፍርበትን ማንነት ታውቃላችሁ?

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (32-40) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በአላህ ላይ መዋሸትና አላህን ማስተባበልን ማውገዝ፤
2. በአላህና በመልዕክተኛው ላይ የሚዋሹ ምንዳቸው ምን ሊሆን እንደሚችል መግለፅ፤
3. በእምነትም ሆነ በአንደበት እንዲሁም በተግባር እውነተኛ መሆን እንዳለበት ማግባባት፤
4. አላህን መፍራት ምን ያህል አስፈላጊና አላህ ዘንድ ከፍተኛ ምንዳ እንዳለው፤
5. አላህ ለባሮቹ በቂ መሆኑን፤
6. ተውሒድን ማፅደቅና ሽርክን ማውገዝ፤
7. አላህ ለነብዩም (ﷺ) ሆነ ለምእምናን የገባውን ቃል መፈፀሙን እንማራለን።

إِنَّآ أَنزَلْنَا عَلَيْكَ ٱلْكِتَٰبَ لِلنَّاسِ بِٱلْحَقِّ ۖ فَمَنِ ٱهْتَدَىٰ فَلِنَفْسِهِۦ ۖ
وَمَن ضَلَّ فَإِنَّمَا يَضِلُّ عَلَيْهَا ۖ وَمَآ أَنتَ عَلَيْهِم بِوَكِيلٍ ﴿٤١﴾

41. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ መጽሐፉን በአንተ ላይ ለሰዎች ጥቅም በእውነት አወረድነው። እናም በሱ የተመራ ሰው ሁሉ ፋይዳው ለነፍሱ ነው። የጠመመም ሰው ጉዳቱ ለራሱ ነው የሚጠመው። አንተም ታስገድዳቸው ዘንድ በእነርሱ ላይ ጠባቂ አይደለህም።

ٱللَّهُ يَتَوَفَّى ٱلۡأَنفُسَ حِينَ مَوۡتِهَا وَٱلَّتِي لَمۡ تَمُتۡ فِي مَنَامِهَاۖ فَيُمۡسِكُ ٱلَّتِي قَضَىٰ عَلَيۡهَا
ٱلۡمَوۡتَ وَيُرۡسِلُ ٱلۡأُخۡرَىٰٓ إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمًّىۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يَتَفَكَّرُونَ ٤٢

**42.** አላህ ነፍሶችን በሞታቸው ጊዜ ይወስዳል። ያችንም ያልሞተችውን ነፍስ በእንቅልፏ ጊዜ ይወስዳታል። ከዚያ ያችን ሞትን የፈረደባትን ነፍስ ይይዛታል። ሌላይቱንም ደግሞ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ ይለቃታል። በዚህ ውስጥ ለሚያስተነትኑ ህዝቦች ሁሉ አያሌ ተአምራት ምልክቶች አሉበት።

أَمِ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ شُفَعَآءَۚ قُلۡ أَوَلَوۡ كَانُواْ لَا يَمۡلِكُونَ شَيۡـٔٗا وَلَا يَعۡقِلُونَ ٤٣
قُل لِّلَّهِ ٱلشَّفَٰعَةُ جَمِيعٗاۖ لَّهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ ثُمَّ إِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ٤٤

**43-44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይልቁንም ቁረይሾች ከአላህ ሌላ አማላጆችን አምላክ አድርገው ያዙ። እነርሱ ምንም የማይችሉና የማያውቁ ቢሆንም አምላክ ታደርጓቸዋላችሁን? በላቸው። ምልጃ ሁሉም የአላህ ብቻ ነው። የሰማያትና የምድር ስልጣንም በእርሱ ብቻ ነው። ከዚያ ወደ እርሱ ትመለሳላችሁ በላቸው።

وَإِذَا ذُكِرَ ٱللَّهُ وَحۡدَهُ ٱشۡمَأَزَّتۡ قُلُوبُ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِۖ وَإِذَا ذُكِرَ ٱلَّذِينَ مِن
دُونِهِۦٓ إِذَا هُمۡ يَسۡتَبۡشِرُونَ ٤٥ قُلِ ٱللَّهُمَّ فَاطِرَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ عَٰلِمَ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ
أَنتَ تَحۡكُمُ بَيۡنَ عِبَادِكَ فِي مَا كَانُواْ فِيهِ يَخۡتَلِفُونَ ٤٦

**45-46.** ላህን ብቻውን በተወሳ ጊዜ የእነዚያ በመጨረሻይቱ ዓለም የማያምኑት ሰዎች ልቦች ይሸማቀቃሉ። ይደናበራሉ። እነዚም ከእርሱ ሌላ የሆኑት ጣዖታት በተወሱ ጊዜ እነርሱ ወዲያውኑ ይደሰታሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰማያትንና ምድርን የፈጠርክ ሩቁንም ቅርቡንም አዋቂ የሆንከው አላህ ሆይ፣ አንተ በባሮችህ መካከል በዚያ ይለያዩበት በነበሩት ነገር ትፈርዳለህ በል።

وَلَوۡ أَنَّ لِلَّذِينَ ظَلَمُواْ مَا فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا وَمِثۡلَهُۥ مَعَهُۥ لَٱفۡتَدَوۡاْ بِهِۦ مِن سُوٓءِ ٱلۡعَذَابِ
يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۚ وَبَدَا لَهُم مِّنَ ٱللَّهِ مَا لَمۡ يَكُونُواْ يَحۡتَسِبُونَ ٤٧ وَبَدَا لَهُمۡ سَيِّـَٔاتُ مَا كَسَبُواْ
وَحَاقَ بِهِم مَّا كَانُواْ بِهِۦ يَسۡتَهۡزِءُونَ ٤٨

**47-48.** ለነዚያ ለበደሉት በምድር ያለው ሁሉ መላውም ከእርሱ ጋር መሰሉም ቢኖራቸው ኖሮ በትንሳኤ ቀን ከቅጣቱ ከፋት የተነሳ በእርሱ ነፍሶቻቸውን በተበገቡበት ነበር። ለእነርሱም ከአላህ ዘንድ ያስቡት ያልነበሩት ሁሉ ይገለጽላቸዋል። ለእነርሱም የሰሯቸው መጥፎቹ ይገለጹላቸዋል። በእነርሱም ላይ በእርሱ ያላግጡበት የነበሩት ቅጣት ይሰፍርባቸዋል።

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (41-48) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ነብዩን (ﷺ) እንዲታገሱ በመምከር ማፅናናት፤
2. የጣኦት አምላኪዎችን ማስረጃ ማንኮታኮት፤
3. ከአላህ ሌላ ካለ አካል ሽምግልናን መጠየቅ ስህተት ስለመሆኑ፤
4. ተውሒድን ሲሰሙ የሚቆጡና ሽርክ ሲሰሙ የሚደሰቱ ሞኞች መሆናቸውን መግለፅ፤
5. ችግሮች ሲበረቱ ወደ አላህ መጠጋት እንደሚገባ፤
6. የቂያማ ዕለት ያለው ቅጣት ብርታት፤
7. በአላህ ህግጋት ላይ ከማፌዝ ማስጠንቀቅን እንማራለን።

فَإِذَا مَسَّ ٱلۡإِنسَٰنَ ضُرّٞ دَعَانَا ثُمَّ إِذَا خَوَّلۡنَٰهُ نِعۡمَةٗ مِّنَّا قَالَ إِنَّمَآ أُوتِيتُهُۥ عَلَىٰ عِلۡمِۭۚ بَلۡ هِيَ
فِتۡنَةٞ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَهُمۡ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٤٩﴾ قَدۡ قَالَهَا ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡ فَمَآ أَغۡنَىٰ عَنۡهُم مَّا
كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ﴿٥٠﴾ فَأَصَابَهُمۡ سَيِّـَٔاتُ مَا كَسَبُواْۚ وَٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ مِنۡ هَٰٓؤُلَآءِ سَيُصِيبُهُمۡ
سَيِّـَٔاتُ مَا كَسَبُواْ وَمَا هُم بِمُعۡجِزِينَ ﴿٥١﴾ أَوَلَمۡ يَعۡلَمُوٓاْ أَنَّ ٱللَّهَ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ
وَيَقۡدِرُۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّقَوۡمٖ يُؤۡمِنُونَ ﴿٥٢﴾ ۞قُلۡ يَٰعِبَادِيَ ٱلَّذِينَ أَسۡرَفُواْ عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمۡ
لَا تَقۡنَطُواْ مِن رَّحۡمَةِ ٱللَّهِۚ إِنَّ ٱللَّهَ يَغۡفِرُ ٱلذُّنُوبَ جَمِيعًاۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٥٣﴾

**49-53.** ሰውንም ጉዳት ባገኘው ጊዜ ይጠራናል። ከዚያ ከእኛ የሆነውን ፀጋ በሰጠነው ጊዜ እርሱን የተሰጠሁት በእውቀት ብቻ ነው ይላል። ይልቁንም እርሷ (ፀጋይቱ) መፈተኛ ናት። ግን አብዛሀኞቻቸው አያውቁም። እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ህዝቦች በእርግጥ ብለዋታል። ይሰሩት የነበሩትም ነገር ከእነርሱ አልጠቀማቸውም። የሰሯቸውም መጥፎዎች ቅጣት አገኟቸው። ከእነዚህም እነዚያ የበደሉት የሰሯቸውን መጥፎዎች ፍዳ በእርግጥ ይነካቸዋል። እነርሱም አምላጮች አይደሉም። አላህ ሲሳዩን ለሚሻው ሰው የሚያሰፋ የሚያጠብም መሆኑን አያውቁምን? በዚህ ውስጥ ለሚያምኑት ህዝቦች ግሳጼዎች አሉበት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው እናንተ በነፍሶቻችሁ ላይ ድንበር ያለፋችሁ ባሮቼ ሆይ፣ ከአላህ እዝነት ተስፋ አትቁረጡ። አላህ ኃጢአቶችን ሁሉ ይምራልና። እነሆ እርሱ መህሪና አዛኝ ነውና።*

✴ ነብዩ (ﷺ) አህመድ፤ አቡ ዳውድ፤ ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሐዲስ «ወንጀል ባትሰሩ ኖሮ አላህ እናንተን አጥፍቶ ወንጀል እየሰሩ ምህረትን የሚለምኑ ሰዎች ባመጣ ነበር» ብለዋል።

وَأَنِيبُوٓاْ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ وَأَسۡلِمُواْ لَهُۥ مِن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَكُمُ ٱلۡعَذَابُ ثُمَّ لَا تُنصَرُونَ ﴿٥٤﴾ وَٱتَّبِعُوٓاْ أَحۡسَنَ مَآ أُنزِلَ إِلَيۡكُم مِّن رَّبِّكُم مِّن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَكُمُ ٱلۡعَذَابُ بَغۡتَةٗ وَأَنتُمۡ لَا تَشۡعُرُونَ ﴿٥٥﴾ أَن تَقُولَ نَفۡسٞ يَٰحَسۡرَتَىٰ عَلَىٰ مَا فَرَّطتُ فِي جَنۢبِ ٱللَّهِ وَإِن كُنتُ لَمِنَ ٱلسَّٰخِرِينَ ﴿٥٦﴾ أَوۡ تَقُولَ لَوۡ أَنَّ ٱللَّهَ هَدَىٰنِي لَكُنتُ مِنَ ٱلۡمُتَّقِينَ ﴿٥٧﴾ أَوۡ تَقُولَ حِينَ تَرَى ٱلۡعَذَابَ لَوۡ أَنَّ لِي كَرَّةٗ فَأَكُونَ مِنَ ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٥٨﴾ بَلَىٰ قَدۡ جَآءَتۡكَ ءَايَٰتِي فَكَذَّبۡتَ بِهَا وَٱسۡتَكۡبَرۡتَ وَكُنتَ مِنَ ٱلۡكَٰفِرِينَ ﴿٥٩﴾

**54-59.** (ሰዎች ሆይ)፣ ቅጣቱ ወደ እናንተ ከመምጣቱና ከዚያ የማትረዱ ከመሆናችሁ በፊት ወደ ጌታችሁ (በመፀፀት) ተመለሱ። ለእርሱም ታዘዙ። እናንተ የማታውቁ ስትሆኑ ቅጣቱ በድንገት ሳይመጣባችሁ በፊት ከጌታችሁ ወደ እናንተ የተወረደውን መልካሙን መጽሐፍ ተከተሉ። በአላህ (የካደች) ነፍስ ሁሉ እኔ ከሚሳለቁት የነበርኩ ስሆን በአላህ በኩል ባጓደልኩት ዋ! ፀፀቴ! ማለቷን (ለመፍራት)።✴ ወይም አላህ በመራኝ ኖሮ ከሚጠነቀቁት ሰዎች እሆን ነበር ማለቷን ለመፍራት። ወይም ቅጣቱን በምታይ ጊዜ ለእኔ ወደ ምድረ አለም አንድ ጊዜ መመለስ በኖረኝና ከበጎ አድራጊዎች በሆንኩ (ማለቷን ለመፍራት) (መልካሙን ተከተሉ)። የለም ተመርተሃል፤ አንቀፆቼ በእርግጥ መጥተውሃል። በእነርሱም አስተባብለሃል፤ ኮርተሃልም። ከከሓዲያንም ሆነሃል (ይባላል)።

✴ በዚህ አንቀፅ ዙሪያ ብዙ የተባለ ቢሆንም:- ሙስሊም የወንጀላቸው ብዛት ከተውበትና ከአላህ ምህረት ተስፋ እንዳያስቆርጣቸው በዚያ አያ አላህ አስጠንቅቋል። ነብዩ (ﷺ) ቢሆኑ ተስፋ መቁረጥን ከታላላቅ ወንጀሎች ፈርጀውታል። ኢብኑ አባስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ስለ ታላላቅ ወንጀሎች ተጠይቀው ሲመልሱ «በአላህ ማጋራት ከአላህ እዝነት ተስፋ መቁረጥና ከአላህ ቅጣት መዘናጋት ናቸው» ብለዋል። ኢብኑ መስዑድም ነብዩ:- «ከታላላቅ ወንጀሎች ሁሉ ይበልጥ ታላቆቹ በአላህ ማሻረክ ከአላህ ቅጣት መዘናጋት ከአላህ እዝነትና ትሩፋት ተስፋ መቁርጥ ናቸው።» ብለዋል።

በዚህ አንቀፅ ዙሪያ ላይ ብዙ ዘገባዎች የተወሱ ቢሆንም የአላህን ምህረት ስፋትና ግዝፈት ለየትኛውም ወንጀለኛ ክፍት መሆኑን የሚሳዩና በአላህ ላይ ሊኖረን የሚገባ ከፍተኛ ተስፋ ሰጭ ቃላት በብዛት እናገኛለን። አላህ ከእኛ የሚፈለገው ዋና ነገር በትክክል በጥፋታችን መፀፀትና ወደ አላህ መመለስ ብቻ ነው። ሰዎች አንድ ጊዜ ከተሳሳቱ ሰይጣን በዚያ ቀዳዳ እየገባ ተስፋ እንዲቆርጡ ያደርጋቸዋል። መሆን ያለበት ግን ስህተታችን የቱንም ያህል ቢገዝፍ ከአላህ ራህመት እንደማይበልጥ ነው ማወቅ ያለብን።

ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከ (54-59) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- አብደላህ ኢብኑ ዑመር አባታቸው ዑመር ለመሰደድ በወሰነ ጊዜ እኔ ሂሻም ኢብኑ ዓልአሲ አያሽ ኢብኑ አቢ ረቢያ ቀጠሮ ያዝን በቀጠሮው ላይ ያልተገኘ ሰው ችግር እንዳጋጠመው ታውቆ ሌሎቹን እንዲጓዙ

ተስማማን። በቀጠሮው መሰረት እኔና ዓያሽ ብን አቢ ረቢዓ ስንመጣ ሂሻም ቀረ መዲና ደርሰን እሱና መሰሎቹ አላህን አውቀው በነብዩም (ﷺ) አምነው የተፈተኑ በመሆናቸው ንሰሃቸው ተቀባይነት ያላቸው አይመስለንም እያልን እናወራ ነበር። እነሱም እንደዚሁ አውቆ ጠፊዎች ስለሆን ንሰሃችን ተቀባይነት የለውም እያሉ ያወሩ ነበር። ይህን አይነቱን ተስፋ አስቆራጭ ንግግሮችን ለማስወገድ ነበር እነዚህ አናቅፅ የወረዱት።

وَيَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ تَرَى ٱلَّذِينَ كَذَبُوا۟ عَلَى ٱللَّهِ وُجُوهُهُم مُّسْوَدَّةٌ ۚ
أَلَيْسَ فِى جَهَنَّمَ مَثْوًى لِّلْمُتَكَبِّرِينَ ﴿٦٠﴾

**60.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በትንሳኤ ቀንም እነዚያ በአላህ ላይ የዋሹትን ፊቶቻቸው የጠቆሩ ሆነው ታያቸዋለህ። በገሀነም ውስጥ ለትዕቢተኞች መኖሪያ የለምን?

وَيُنَجِّى ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوْا۟ بِمَفَازَتِهِمْ لَا يَمَسُّهُمُ ٱلسُّوٓءُ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿٦١﴾
ٱللَّهُ خَـٰلِقُ كُلِّ شَىْءٍ ۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ وَكِيلٌ ﴿٦٢﴾

**61-62.** እነዚያም የተጠነቀቁትን በማግኛቸው ስፍራ ሆነው አላህ ያድናቸዋል፤ ክፉ ነገር አይነካቸውም። እነርሱም አያዝኑም። አላህ የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ አስተናባሪ ነው።

لَّهُۥ مَقَالِيدُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۗ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِـَٔايَـٰتِ ٱللَّهِ أُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَـٰسِرُونَ ﴿٦٣﴾

**63.** የሰማያትና የምድር (ድልብ) መከፈቻዎች የእርሱ ብቻ ናቸው። እነዚያም በአላህ አንቀፆች የካዱት እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎች ናቸው።

قُلْ أَفَغَيْرَ ٱللَّهِ تَأْمُرُوٓنِّىٓ أَعْبُدُ أَيُّهَا ٱلْجَـٰهِلُونَ ﴿٦٤﴾ وَلَقَدْ أُوحِىَ إِلَيْكَ
وَإِلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِكَ لَئِنْ أَشْرَكْتَ لَيَحْبَطَنَّ عَمَلُكَ وَلَتَكُونَنَّ مِنَ ٱلْخَـٰسِرِينَ ﴿٦٥﴾
بَلِ ٱللَّهَ فَٱعْبُدْ وَكُن مِّنَ ٱلشَّـٰكِرِينَ ﴿٦٦﴾

**64-66.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አናንተ መሃይማን ሆይ፣ ከአላህ ሌላን እንድገዛ ታዙኛላችሁን? በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታበሳል። በእርግጥም ከከሃዲዎቹ ትሆናለህ በማለት ወደ አንተና እነዚያ ከአንተ በፊት ወደ ነበሩት ሰዎች በእርግጥ ተወርዷል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይልቅ አላህን ብቻ ተገዛም። ከአመስጋኞችም ሁን።*

✴ ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከ (60-64) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ሙሽሪኮች ነብዩ (ﷺ) አባቶችህንና አያቶችህን ተሳስተዋል ትላለህን ብለው በመጠየቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ሱዩጢ)

وَمَا قَدَرُواْ ٱللَّهَ حَقَّ قَدْرِهِۦ وَٱلْأَرْضُ جَمِيعًا قَبْضَتُهُۥ يَوْمَ ٱلْقِيَـٰمَةِ وَٱلسَّمَـٰوَٰتُ مَطْوِيَّـٰتٌۢ بِيَمِينِهِۦ ۚ سُبْحَـٰنَهُۥ وَتَعَـٰلَىٰ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٦٧﴾

67. አላህንም በትንሳኤው ቀን ምድር በመላ ጭብጡ ስትሆንና ሰማያትም በቀኝ እጁ* የሚጠቀለሉ ሲሆኑ ከእርሱ ጋር ሌላን በማጋራታቸው ተገቢ ክብሩን አላከበሩትም፡፡ ከሚያጋሩት ጠራ ላቀም፡፡

✴ ይህና ይህን መሰል የአላህን ባህሪና ስሞች የሚናገሩ የቁርአን አናቅጾችና ሐዲሶች ተፍሲር በተመለከተ አላህን ከማንም ከምንም ፍጡር ጋር ሳናመሳስልና አላህን ከጉድለት በማጥራት በሰለፎች ግንዛቤና አረዳድ እናስቀምጣለን እዚህ ላይ በጣም ልንጠነቀቅ የሚገባው ነገር ፤ኛ እንዴት? (ከይፍ?) እና ለምን? የሚሉ ጥያቄዎች ሁሉ በፍጹም የተከለከሉ ናቸው 2ኛ አላህ በማንም በምንም አይመሳሰልም በዚህ ዙሪያ በሰፊው ለመረዳት በሱረቱ አል አዕራፍ (54) አንቀጽ ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ ተመልከት፡፡

وَنُفِخَ فِى ٱلصُّورِ فَصَعِقَ مَن فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَمَن فِى ٱلْأَرْضِ إِلَّا مَن شَآءَ ٱللَّهُ ۖ ثُمَّ نُفِخَ فِيهِ أُخْرَىٰ فَإِذَا هُمْ قِيَامٌ يَنظُرُونَ ﴿٦٨﴾ وَأَشْرَقَتِ ٱلْأَرْضُ بِنُورِ رَبِّهَا وَوُضِعَ ٱلْكِتَـٰبُ وَجِا۟ىٓءَ بِٱلنَّبِيِّـۧنَ وَٱلشُّهَدَآءِ وَقُضِىَ بَيْنَهُم بِٱلْحَقِّ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿٦٩﴾ وَوُفِّيَتْ كُلُّ نَفْسٍ مَّا عَمِلَتْ وَهُوَ أَعْلَمُ بِمَا يَفْعَلُونَ ﴿٧٠﴾

68-70. በቀንዱም ይነፋል፡፡ በሰማያት ውስጥ ያለው ፍጡርና በምድርም ውስጥ ያለው ፍጡር ሁሉ አላህ የሻው ሲቀር በድንጋጤ ይሞታል፡፡ ከዚያ በእርሱ ሌላ መነፋት ይነፋል፡፡ ወዲያውኑም እነርሱ (የሚሰራባቸውን) የሚጠባበቁ ሆነው* ቋሚዎች ይሆናሉ፡፡ ምድርም በጌታዋ ብርሃን ታበራለች፤ መፅሐፉም ይቀርባል ነብያትና ምስክሮችም ይመጣሉ፡፡ በመካከላቸውም በእውነት ይፈረዳል፡፡ እነርሱም አይበደሉም፡፡ ነፍስም ሁሉ የሰራቸውን ስራ ትሞላለች (ትሰፈራለች)፡፡ እርሱም የሚሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነው፡፡

✴ (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት»የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የመጨረሻ ጥሩንባ ከተነፋ በኋላ በቅድሚያ ራሱን ከፍ የማደርገው እኔ ነኝ፡፡ ሙሳም በተከበረው ዙፋኑ ላይ ተንጠልጥሎ አየዋለሁ፡፡ ነገር ግን በሁለተኛው ጥሩንባ መነፋት በኋላ ይንጠልጠል ወይም ከዚያ በፊት ይሁን አላውቅም»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- «በሁለቱ ጥሩንባ መነፋቶች መካከል አርባ አሉ» ሰዎችም «አቡ ሁረይራህ ሆይ! አርባ ቀናት ናቸውን?» አሉኝ፡፡ እኔም አሁንም ለመመለስ እምቢ አልኩኝና «ከመቀመጫው ላይ ካላቸው ቁራጭ አጥንት በስተቀር ሁሉንም የሰው ልጅ አካል ይጠፋል፡፡ ይበሰብሳልም፡፡ አላህም ከዚህች አጥንት የሰው ልጅን ዳግመኛ ይፈጥረዋል፡፡»

وَسِيقَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ إِلَىٰ جَهَنَّمَ زُمَرًاۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءُوهَا فُتِحَتۡ أَبۡوَٰبُهَا وَقَالَ لَهُمۡ خَزَنَتُهَآ
أَلَمۡ يَأۡتِكُمۡ رُسُلٞ مِّنكُمۡ يَتۡلُونَ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِ رَبِّكُمۡ وَيُنذِرُونَكُمۡ لِقَآءَ يَوۡمِكُمۡ
هَٰذَاۚ قَالُواْ بَلَىٰ وَلَٰكِنۡ حَقَّتۡ كَلِمَةُ ٱلۡعَذَابِ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ ٧١ قِيلَ ٱدۡخُلُوٓاْ أَبۡوَٰبَ جَهَنَّمَ
خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ فَبِئۡسَ مَثۡوَى ٱلۡمُتَكَبِّرِينَ ٧٢

**71-72.** እነዚያ በአላህ የካዱትም የተከፋፈሉ ጭፍሮች ሆነው ወደ ገሀነም ይነዳሉ፤ በመጧትም ጊዜ በሮቿ ይከፈታሉ። ወደሷ በመጡም ጊዜ ዘበኞቹም ከእንናንተ የሆነ መልዕክተኞች የጌታችሁን አንቀፆች በእናንተ ላይ የሚያነቡላችሁ የዚህንም ቀን መገናኘት የሚያስጠነቅቋችሁ አልመጡዋችሁምን? ይሏቸዋል፤ የለም መጥተውልናል። ግን የቅጣቲቱ ቃል በከሓዲያን ላይ ተረጋገጠች ይላሉ። የገሀነምን በሮች በውስጧ ዘወታሪዎች ስትሆኑ ግቡ የትዕቢተኞችም መኖሪያ ምን ትከፋ! ይባላሉ።

وَسِيقَ ٱلَّذِينَ ٱتَّقَوۡاْ رَبَّهُمۡ إِلَى ٱلۡجَنَّةِ زُمَرًاۖ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءُوهَا وَفُتِحَتۡ أَبۡوَٰبُهَا وَقَالَ لَهُمۡ
خَزَنَتُهَا سَلَٰمٌ عَلَيۡكُمۡ طِبۡتُمۡ فَٱدۡخُلُوهَا خَٰلِدِينَ ٧٣ وَقَالُواْ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ ٱلَّذِي صَدَقَنَا
وَعۡدَهُۥ وَأَوۡرَثَنَا ٱلۡأَرۡضَ نَتَبَوَّأُ مِنَ ٱلۡجَنَّةِ حَيۡثُ نَشَآءُۖ فَنِعۡمَ أَجۡرُ ٱلۡعَٰمِلِينَ ٧٤

**73-74.** እነዚያም ጌታቸውን የፈሩት የተከፋፈሉ ጭፍሮች ሆነው ወደ ገነት ይነዳሉ። በመጧትም ጊዜ ደጃፎቿ የተከፈቱ ሲሆኑ ዘበኞቿም ለእነርሱ ሰላም በእናንተ ላይ ይሁን ተዋባችሁ፤ ዘወታሪዎች ሆናችሁ ግቧት። ባሏቸው ጊዜ ይገቧታል። ምስጋና ሁሉ ለአላህ ለዚያ ተስፋ ቃሉን ለሞላልን፤ የገነትን ምድር በምንሻው ስፍራ የምንሰፍር ስንሆን ላወረሰን ይገባው ይላሉም የሰሪዎችም ምንዳ ምን ያምር ነው፤

وَتَرَى ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ حَآفِّينَ مِنۡ حَوۡلِ ٱلۡعَرۡشِ يُسَبِّحُونَ بِحَمۡدِ رَبِّهِمۡۚ
وَقُضِيَ بَيۡنَهُم بِٱلۡحَقِّۚ وَقِيلَ ٱلۡحَمۡدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٧٥

**75.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መላዕክትንም በጌታቸው ምስጋና ቀላቅለው የሚያጠሩ ሲሆኑ በአርሹ ዙሪያ ከባቢዎች ሆነው ታያለህ። በመካከላቸውም በእውነት ይፈርዳል፤ ይባላልም፤ ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይገባው።

**ከጭፍራዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (49-75) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የክህደት ሰዎች በህይወታቸው ሁሉ የተምታቱ ስለመሆናቸው፤
2. የትኛውም ሙሲባ ሁሉ ይብዛም ይነስም ይታወቅም ይደበቅ ከወንጀል ጋር የተያያዘ ስለ መሆኑ፤
3. አላህ ለግለሰቦችም ሆነ ለህዝቦች ሲሳይን መለገስም ሆነ መንፈግ ከአላህ ውዴታን ወይም ጥላቻን እንደሚያመለክት፤
4. አላህ ለባሮቹ የዋላቸውን ውለታዎች በግልፅ ማሳየት፤
5. ሩህሩሁ አላህ ለወንጀለኞች ባሮቹ ያደረገው የንሰሃ ግቡ ጥሪ፤
6. ሙቶ መነሳት ሀቅነት ማረጋገጥ፤
7. ንሰሀ መግባት ላይ መፋጠን ተገቢ ስለመሆኑ፤
8. በኢስላም ገርገሮችን እየፈለጉ ከመያዝ ማስጠንቀቅ፤
9. ወንጀልን ለመስራት ከአላህ ተገደን ነው የሚሉትን የአል. ጅብሬያ መዝሀብ ተከታይ ሀሳብ ማፍረስ፤
10. አላህን መፍራት ያለው ትልቅ ምንዳ፤
11. የእውነት ምልክት ደግሞ ፊት መጥቆር ስለ መሆኑ፤
12. ከአላህ ቁጥጥር ማንም እንደማይወጣ፤
13. የአላህን ህግጋት ማክበር ግዴታ ስለ መሆኑ፤
14. የአላህን ትልቅነት የሚያንፀባርቁ ክንውኖች፤
15. በትንሳኤ ዕለት የሚሰጠውን የአላህ ፍትህ ማሳወቅ፤
16. የዚህች ኡመትን ትልቅነት፤
17. የእሳት ሰዎችን እንዴት እንደሚያዋርዳቸው፤
18. ከአላህ አምልኮ ማስጠንቀቅ፤
19. አላህ ቅን ባሮቹን እንደሚያከብራቸው፤
20. የትንሳኤ ቀን ምርመራ የእሳት ሰዎች ወደ እሳት የጀነት ሰዎች ወደ ጀነት በመለየት እንደሚሆኑ፤
21. ሁሉን ነገር አላህን በማመስገን መደምደም ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የጭፍራዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (40)
## የመሃሪው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ጋፊር)

سُورَةُ غَافِرٍ

በመካ የወረደ ምዕራፍ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (85) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

حمٓ ١ تَنزِيلُ ٱلۡكِتَٰبِ مِنَ ٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡعَلِيمِ ٢ غَافِرِ ٱلذَّنۢبِ وَقَابِلِ ٱلتَّوۡبِ شَدِيدِ
ٱلۡعِقَابِ ذِي ٱلطَّوۡلِۖ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ إِلَيۡهِ ٱلۡمَصِيرُ ٣

**1-3.** ሓ፤ ሚይም፤* የመጽሐፉን መውረድ አሸናፊ አዋቂ ከሆነው ከአላህ ብቻ ነው። ኃጢአት መሀሪና ፀፀትን ተቀባይ ቅጣቱ ብርቱ የልግስና ባለቤት ከሆነው አላህ ብቻ የወረደ ነው። ከእርሱ በቀር አምላክ የለም። መመለሻውም ወደ እርሱ ብቻ ነው።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርአን ታአምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

مَا يُجَٰدِلُ فِيٓ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ إِلَّا ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فَلَا يَغۡرُرۡكَ تَقَلُّبُهُمۡ فِي ٱلۡبِلَٰدِ ٤ كَذَّبَتۡ
قَبۡلَهُمۡ قَوۡمُ نُوحٖ وَٱلۡأَحۡزَابُ مِنۢ بَعۡدِهِمۡۖ وَهَمَّتۡ كُلُّ أُمَّةِۭ بِرَسُولِهِمۡ لِيَأۡخُذُوهُۖ وَجَٰدَلُواْ
بِٱلۡبَٰطِلِ لِيُدۡحِضُواْ بِهِ ٱلۡحَقَّ فَأَخَذۡتُهُمۡۖ فَكَيۡفَ كَانَ عِقَابِ ٥ وَكَذَٰلِكَ حَقَّتۡ كَلِمَتُ
رَبِّكَ عَلَى ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَنَّهُمۡ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِ ٦

**4-6.** እነዚያ በአላህ አንቀፆች የካዱት ቢሆኑ እንጂ ማንም (በመዝለፍ) አይከራከርም። በያገሮችም ውስጥ መዘዋወራቸው አይሸንግልህ። ከእነርሱ በፊት የኑህ ህዝቦች ከኋላቸውም አህዛቦች አስተባበሉ። ህዝቦችም ሁሉ መልዕክተኛቸውን ሊይዙ አሰቡ፤ በውሸትም በእርሱ እውነትን ሊያጠፉበት ተከራከሩ። ያዝኳቸውም ታዲያ ቅጣቴ እንዴት ነበር? እነዚያም የጌታህ ቃል በእነዚያ በአላህ በካዱት ላይ እነርሱ የእሳት ጓዶች ናቸው ማለት ተረጋገጠች።

ٱلَّذِينَ يَحۡمِلُونَ ٱلۡعَرۡشَ وَمَنۡ حَوۡلَهُۥ يُسَبِّحُونَ بِحَمۡدِ رَبِّهِمۡ وَيُؤۡمِنُونَ بِهِۦ وَيَسۡتَغۡفِرُونَ
لِلَّذِينَ ءَامَنُواْۖ رَبَّنَا وَسِعۡتَ كُلَّ شَيۡءٖ رَّحۡمَةٗ وَعِلۡمٗا فَٱغۡفِرۡ لِلَّذِينَ تَابُواْ وَٱتَّبَعُواْ سَبِيلَكَ
وَقِهِمۡ عَذَابَ ٱلۡجَحِيمِ ٧ رَبَّنَا وَأَدۡخِلۡهُمۡ جَنَّٰتِ عَدۡنٍ ٱلَّتِي وَعَدتَّهُمۡ وَمَن صَلَحَ مِنۡ
ءَابَآئِهِمۡ وَأَزۡوَٰجِهِمۡ وَذُرِّيَّٰتِهِمۡۚ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٨

**7-8.** እነዚያ ዐርሹን የሚሸከሙት እነዚያም በዙሪያው ያሉት በጌታቸው ምስጋና ያወድሳሉ፤ በእርሱም ያምናሉ ጌታችን ሆይ! ነገሩን ሁሉ በእዝነትና በእውቀት ከበሃል፤ ስለዚህ ለእነዚያ ለተፀፀቱት መንገድህንም ለተከተሉት ምህረት አድርግላቸው፤ የእሳትንም ቅጣት ጠብቃቸው፤ እያሉ ለእነዚያ ላመኑት ምህረትን ይለምናሉ። ጌታችን ሆይ! እነርሱም ከአባቶቻቸውና ከሚስቶቻቸውም ከዝርዮቻቸውም የበጀውን ሁሉ እነዚያን ቃል የገባህላቸውን የመኖሪያ ገነቶች አግባቸው፤ አንተ አሸናፊ፣ ጥበበኛ አንተ ነህና።

وَقِهِمُ ٱلسَّيِّـَٔاتِۚ وَمَن تَقِ ٱلسَّيِّـَٔاتِ يَوۡمَئِذٖ فَقَدۡ رَحِمۡتَهُۥۚ وَذَٰلِكَ هُوَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ٩

**9.** ከቅጣቶችም ጠብቃቸው፤ በዚያ ቀንም የምትጠብቀውን ሰው በእርግጥ አዘንክለት። ይህም እርሱ ታላቅ ማግኘት ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُنَادَوۡنَ لَمَقۡتُ ٱللَّهِ أَكۡبَرُ مِن مَّقۡتِكُمۡ أَنفُسَكُمۡ إِذۡ تُدۡعَوۡنَ إِلَى
ٱلۡإِيمَٰنِ فَتَكۡفُرُونَ ١٠ قَالُواْ رَبَّنَآ أَمَتَّنَا ٱثۡنَتَيۡنِ وَأَحۡيَيۡتَنَا ٱثۡنَتَيۡنِ فَٱعۡتَرَفۡنَا بِذُنُوبِنَا فَهَلۡ
إِلَىٰ خُرُوجٖ مِّن سَبِيلٖ ١١ ذَٰلِكُم بِأَنَّهُۥٓ إِذَا دُعِيَ ٱللَّهُ وَحۡدَهُۥ كَفَرۡتُمۡ وَإِن يُشۡرَكۡ بِهِۦ
تُؤۡمِنُواْۚ فَٱلۡحُكۡمُ لِلَّهِ ٱلۡعَلِيِّ ٱلۡكَبِيرِ ١٢

**10-12.** እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ወደ እምነት በምትጠሩና በምትክዱ ጊዜ አላህ እናንተን መጥላቱ ነፍሶቻችሁን ዛሬ ከመጥላታችሁ የበለጠ ነው በማለት ይጠራሉ። ጌታችን ሆይ፣ ሁለትን ሞት አሞትከን። ሁለትንም ሕይወት ህያው አደረግከን። በኃጢአቶቻችንም መሰከርን ታዲያ (ከእሳት) ወደ መውጣት መንገድ አለን? ይላሉ። ከሀዲያን ሆይ፣ ይሃችሁ እነሆ አላህ ብቻውን በተጠራ ጊዜ ስለ ካዳችሁ በእርሱም ተጋሪ ቢደረግ የምታምኑ ስለሆናችሁ ነው። ስለዚህ ፍርዱ ከፍተኛ ታላቅ* ለሆነው አላህ ብቻ ነው።

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ እንዳስተላለፉት፡- «አንዲት ነገር ተናገሩ እኔም አንዲት ነገር ተናገርኩ። የአላህ መልዕክተኛ «አንድ ሰው ከአላህ ሌላ ያለን ነገር እያመለከ ከሞተ በእርግጥ እሳት ውስጥ ገብቷል» አሉ። እኔ ደግሞ «ከአላህ ሌላ ያለን ነገር ሳያመልክ የሞተ በእርግጥ ጀነት ገብቷል» አልኩኝ።

هُوَ ٱلَّذِى يُرِيكُمْ ءَايَٰتِهِۦ وَيُنَزِّلُ لَكُم مِّنَ ٱلسَّمَآءِ رِزْقًاۚ وَمَا يَتَذَكَّرُ إِلَّا مَن يُنِيبُ ﴿١٣﴾
فَٱدْعُواْ ٱللَّهَ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ وَلَوْ كَرِهَ ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿١٤﴾

**13-14.** (ሰዎች ሆይ)፣ እርሱ ያ ለአምላክነቱ ምልክቶችን የሚያሳያችሁ ለእናንተም ከሰማይ ሲሳይን የሚያወርድላችሁ ነው። ወደርሱም የሚመለስ ሰው ቢሆን እንጂ ሌላው አይገሰፅም። አላህንም ከሓዲያን ቢጠሉትም ሃይማኖትን ለእርሱ አጥሪዎች ሆናችሁ ተገዙ።

رَفِيعُ ٱلدَّرَجَٰتِ ذُو ٱلْعَرْشِ يُلْقِى ٱلرُّوحَ مِنْ أَمْرِهِۦ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ مِنْ عِبَادِهِۦ
لِيُنذِرَ يَوْمَ ٱلتَّلَاقِ ﴿١٥﴾ يَوْمَ هُم بَٰرِزُونَۖ لَا يَخْفَىٰ عَلَى ٱللَّهِ مِنْهُمْ شَىْءٌۚ
لِّمَنِ ٱلْمُلْكُ ٱلْيَوْمَۖ لِلَّهِ ٱلْوَٰحِدِ ٱلْقَهَّارِ ﴿١٦﴾

**15-16.** እርሱ ደረጃዎችን ከፍ አድራጊ የዐርሹ ባለቤት ነው። የመገናኛውን ቀን ያስፈራራ ዘንድ ከባሮቹ በሚሻው ሰው ላይ ከትዕዛዙ ራዕይን ያወርዳል። እነርሱ ከመቃብር በሚወጡበት ቀን በአላህ ላይ ከእነርሱ ምንም ነገር አይደበቅም። ንግስናው ዛሬ ለማን ነው? ይባላል። ለአሸናፊው ለአንዱ አላህ ብቻ ነው (ይባላል)።

ٱلْيَوْمَ تُجْزَىٰ كُلُّ نَفْسٍۭ بِمَا كَسَبَتْۚ لَا ظُلْمَ ٱلْيَوْمَۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَرِيعُ ٱلْحِسَابِ ﴿١٧﴾

**17.** ዛሬ ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ ትመነዳለች፤ ዛሬ በደል የለም። አላህ በእርግጥ ምርመራው ፈጣን ነው (ይባላል)።

**ከመሃሪው ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-17) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ቁርኣን የወረደው ከአላህ እንደሆነ፤
2. የአላህን ትልቅነት ማረጋገጥ፤
3. ተውሒድንና ሙቶ መነሳት መነሳትን ማረጋገጥ፡
4. አላህ ለጥፋተኞች ጊዜ ይሰጣል እንጂ በሙሉ እንደማይተዋቸው፡
5. የእምነት ትልቅነት፤
6. ሁል ጊዜ ዚክርና አላህን ማጥራት ተገቢ ስለመሆን፤
7. አላህ አማኞችን በጀነት እንደሚሰበስባቸው፤
8. የቂያማ ቀን ምንም ምክንያት ማቅረብ እንደማይቻል ቢያቀርቡም ተቀባይነት እንደሌለው፤
9. ተውሒድን ማፅደቅና ሽርክን ማውገዝ፤
10. አላህ ለባሮቹ የዋለው አያሌ ውለታ፤
11. ዒባዳን ለአላህ ማጥራት ተገቢ ስለመሆኑ፤
12. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ እንማራለን፤

وَأَنذِرۡهُمۡ يَوۡمَ ٱلۡأٓزِفَةِ إِذِ ٱلۡقُلُوبُ لَدَى ٱلۡحَنَاجِرِ كَٰظِمِينَۚ مَا لِلظَّٰلِمِينَ مِنۡ حَمِيمٖ
وَلَا شَفِيعٖ يُطَاعُ ﴿١٨﴾ يَعۡلَمُ خَآئِنَةَ ٱلۡأَعۡيُنِ وَمَا تُخۡفِي ٱلصُّدُورُ ﴿١٩﴾ وَٱللَّهُ يَقۡضِي بِٱلۡحَقِّۖ
وَٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ مِن دُونِهِۦ لَا يَقۡضُونَ بِشَيۡءٍۗ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ ﴿٢٠﴾

**18-20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቅርቢቱንም የትንሳኤ ቀን ልቦች ጭንቀትን የተሞሉ ሆነው ላንቃዎች ዘንድ የሚደርሱበት ጊዜ አስጠንቅቃቸው፡፡ ለበዳዮች ምንም ወዳጅና ተሰሚ አማላጅ የላቸውም፡፡ አላህ የዓይኖችን ክዳት ልቦችም የሚደብቁትን ሁሉ ያውቃል፡፡ አላህም በእውነት ይፈርዳል፡፡ እነዚያም ከእርሱ ሌላ የሚገዟቸው በምንም አይፈርዱም፡፡ አላህ እርሱ ሰሚ፤ ተመልካች ነው፡፡

۞ أَوَلَمۡ يَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَيَنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ كَانُواْ مِن قَبۡلِهِمۡۚ كَانُواْ هُمۡ
أَشَدَّ مِنۡهُمۡ قُوَّةٗ وَءَاثَارٗا فِي ٱلۡأَرۡضِ فَأَخَذَهُمُ ٱللَّهُ بِذُنُوبِهِمۡ وَمَا كَانَ لَهُم مِّنَ ٱللَّهِ مِن
وَاقٖ ﴿٢١﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ كَانَت تَّأۡتِيهِمۡ رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَكَفَرُواْ فَأَخَذَهُمُ ٱللَّهُۚ إِنَّهُۥ قَوِيّٞ
شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ﴿٢٢﴾

**21-22.** የእነዚያን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ፍፃሜ እንዴት እንደነበረ ይመለከቱ ዘንድ በምድር ላይ አይሄዱምን? በሀይልና በምድር ላይ በተዋቸው ምልክቶች፡፡ ከእነርሱም ይበልጥ የበረቱ ነበሩ፡፡ አላህም በኃጢአቶቻቸው ያዛቸው ለእነርሱም ከአላህ ቅጣት ምንም ጠባቂ አልነበራቸውም፡፡ ይህ (መያዝ) እነርሱ መልዕክተኞቻቸው በተዐምራቶች ይመጡባቸው ስለ ነበሩና ስለካዱ ነው፡፡ አላህም ያዛቸው፤ እርሱ ኃያል፤ ቅጣቱ ብርቱ ነውና፡፡

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَا وَسُلۡطَٰنٖ مُّبِينٍ ﴿٢٣﴾ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ وَهَٰمَٰنَ وَقَٰرُونَ فَقَالُواْ
سَٰحِرٞ كَذَّابٞ ﴿٢٤﴾ فَلَمَّا جَآءَهُم بِٱلۡحَقِّ مِنۡ عِندِنَا قَالُواْ ٱقۡتُلُوٓاْ أَبۡنَآءَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مَعَهُۥ
وَٱسۡتَحۡيُواْ نِسَآءَهُمۡۚ وَمَا كَيۡدُ ٱلۡكَٰفِرِينَ إِلَّا فِي ضَلَٰلٖ ﴿٢٥﴾ وَقَالَ فِرۡعَوۡنُ ذَرُونِيٓ أَقۡتُلۡ
مُوسَىٰ وَلۡيَدۡعُ رَبَّهُۥٓۖ إِنِّيٓ أَخَافُ أَن يُبَدِّلَ دِينَكُمۡ أَوۡ أَن يُظۡهِرَ فِي ٱلۡأَرۡضِ ٱلۡفَسَادَ ﴿٢٦﴾
وَقَالَ مُوسَىٰٓ إِنِّي عُذۡتُ بِرَبِّي وَرَبِّكُم مِّن كُلِّ مُتَكَبِّرٖ لَّا يُؤۡمِنُ بِيَوۡمِ ٱلۡحِسَابِ ﴿٢٧﴾

**23-27.** ሙሳንም በታዐምራቶቻችንና በግልፅ ማስረጃ በእርግጥ ላክነው፡፡ ወደ ፈርዖን ወደ ሃማን እና ወደ ቃሩንም ላክነው፡፡ ድግምተኛ እና ውሸታም ነው አሉ፡፡ ከእኛ ዘንድ እውነትን ይዞ በመጣላቸው ጊዜ የእነዚያን ከእርሱ ጋር ያመኑት ሰዎች ወንድ ልጆች ግደሉ፤ ሴቶቻቸውንም አስቀሩ አሉ፤ የከሓዲያንም ተንኮል በጥፋት ውስጥ እንጂ አይደለም፡፡ ፈርዖንም ተወኝ፤ ሙሳን ልግደል፡፡ ጌታውንም ይጥራ፡፡ ያድነው እንደሆነ፤ እኔ ሃይማኖታችሁን ሊለውጥ ወይም በምድር ውስጥ ጥፋትን ሊያሰራጭ እፈራለሁና አለ፡፡ ሙሳም እኔ በምርመራው ቀን ከማያምን ትዕቢተኛ ሁሉ በጌታዬና በጌታችሁ ተጠበቅሁ አለ፡፡

وَقَالَ رَجُلٌ مُّؤۡمِنٌ مِّنۡ ءَالِ فِرۡعَوۡنَ يَكۡتُمُ إِيمَٰنَهُۥٓ أَتَقۡتُلُونَ رَجُلًا أَن يَقُولَ رَبِّيَ ٱللَّهُ وَقَدۡ
جَآءَكُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ مِن رَّبِّكُمۡۖ وَإِن يَكُ كَٰذِبٗا فَعَلَيۡهِ كَذِبُهُۥۖ وَإِن يَكُ صَادِقٗا يُصِبۡكُم
بَعۡضُ ٱلَّذِي يَعِدُكُمۡۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهۡدِي مَنۡ هُوَ مُسۡرِفٞ كَذَّابٞ ﴿٢٨﴾ يَٰقَوۡمِ لَكُمُ ٱلۡمُلۡكُ
ٱلۡيَوۡمَ ظَٰهِرِينَ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَمَن يَنصُرُنَا مِنۢ بَأۡسِ ٱللَّهِ إِن جَآءَنَاۚ قَالَ فِرۡعَوۡنُ مَآ أُرِيكُمۡ
إِلَّا مَآ أَرَىٰ وَمَآ أَهۡدِيكُمۡ إِلَّا سَبِيلَ ٱلرَّشَادِ ﴿٢٩﴾ وَقَالَ ٱلَّذِيٓ ءَامَنَ يَٰقَوۡمِ إِنِّيٓ أَخَافُ
عَلَيۡكُم مِّثۡلَ يَوۡمِ ٱلۡأَحۡزَابِ ﴿٣٠﴾ مِثۡلَ دَأۡبِ قَوۡمِ نُوحٖ وَعَادٖ وَثَمُودَ وَٱلَّذِينَ مِنۢ بَعۡدِهِمۡۚ وَمَا
ٱللَّهُ يُرِيدُ ظُلۡمٗا لِّلۡعِبَادِ ﴿٣١﴾

**28-31.** ከፈርዖን ቤተሰቦች አንድ እምነትን የሚደብቅ ምዕመን ሰው አለ ሰውየውን ከጌታችሁ በታዐምራቶች በእርግጥ የመጣላችሁ ሲሆን ጌታዬ አላህ ነው ስለሚል ትገድሉታላችሁን? ውሸታምም ቢሆን ውሸቱ በእርሱ ላይ ነው፡፡ እውነተኛ ቢሆን ግን የእዚያ የሚያስፈራራችሁ ከፊሉ ያገኛችኋል፡፡ አላህ እርሱ ያንን ድንበር አላፊና ውሸታም የሆነውን አይምርምና፡፡ ወገኖቼ ሆይ፣ በምድር ላይ አሸናፊዎች ስትሆኑ ዛሬ መንግስትነት የእናንተ ነው፡፡ ታዲያ ከአላህ ቅጣት ቢመጣብን የሚያድነን ማን ነው? አለ፡፡ ፈርዖን የማየውን እንጂ አላመለከታችሁም፤ ቅኑን መንገድ እንጂ አልመራችሁም አላቸው፡፡ ያም ያመነው ሰው አለ፡- እኔ በእናንተ ላይ የአህዛብን ቀን ብጤ እፈራላችኋለሁ፡፡ የ (ነብዩ) ኑህን ህዝቦች የዓድንና የሰሙድም የእነዚያን ከኋላቸው የነበሩትን ህዝቦች ልማድ ብጤ እፈራላችኋለሁ፡፡ አላህም ለባሮቹ መበደልን የሚሻ ጌታ አይደለም፡፡

وَيَٰقَوۡمِ إِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ يَوۡمَ ٱلتَّنَادِ ﴿٣٢﴾ يَوۡمَ تُوَلُّونَ مُدۡبِرِينَ مَا لَكُم مِّنَ ٱللَّهِ مِنۡ عَاصِمٖۗ
وَمَن يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِنۡ هَادٖ ﴿٣٣﴾ وَلَقَدۡ جَآءَكُمۡ يُوسُفُ مِن قَبۡلُ بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَمَا زِلۡتُمۡ فِي
شَكّٖ مِّمَّا جَآءَكُم بِهِۦۖ حَتَّىٰٓ إِذَا هَلَكَ قُلۡتُمۡ لَن يَبۡعَثَ ٱللَّهُ مِنۢ بَعۡدِهِۦ رَسُولٗاۚ كَذَٰلِكَ يُضِلُّ
ٱللَّهُ مَنۡ هُوَ مُسۡرِفٞ مُّرۡتَابٌ ﴿٣٤﴾ ٱلَّذِينَ يُجَٰدِلُونَ فِيٓ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ بِغَيۡرِ سُلۡطَٰنٍ أَتَىٰهُمۡۖ كَبُرَ
مَقۡتًا عِندَ ٱللَّهِ وَعِندَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْۚ كَذَٰلِكَ يَطۡبَعُ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ قَلۡبِ مُتَكَبِّرٖ جَبَّارٖ ﴿٣٥﴾

**32-35.** ወገኖቼ ሆይ! እኔ በእናንተ ላይ የመጠራሪያን ቀን እፈራለሁ። ወደ ኋላ ዞራችሁ በምትሸሹበት ቀን፤ ለእናንተ ከአላህ ቅጣት ምንም ጠባቂ የላችሁም፤ አላህም የሚያጠመው ሰው ለእርሱ ምንም አቅኚ የለውም። ዩሱፍም ከዚህ በፊት ግልፅ ማስረጃዎችን በእርግጥ አመጣላችሁ። ከዚያ እርሱ ካመጣላችሁ ነገር ከመጠራጠር አልተወገዳችሁም። በጠፋም ጊዜ አላህ ከእርሱ ኋላ መልዕክተኛን በጭራሽ አይልክም አላችሁ፤ አላህ እነዚህን ድንበር አላፊ ተጠራጣሪ የሆነን ሰው ያሳስታል። እነዚያ የመጣላቸው አስረጅ ሳይኖር በአላህ ታዕምራቶች የሚከራከሩ (ክርክራቸው) አላህ ዘንድና እነዚያም አመኑት ዘንድ መጠላቱ በጣም ተለቀ። እንደዚሁ አላህ በኩሩ ጨካኝ ሰው ልብ ሁሉ ላይ ያትማል።

وَقَالَ فِرۡعَوۡنُ يَٰهَٰمَٰنُ ٱبۡنِ لِي صَرۡحٗا لَّعَلِّيٓ أَبۡلُغُ ٱلۡأَسۡبَٰبَ ﴿٣٦﴾ أَسۡبَٰبَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ فَأَطَّلِعَ إِلَىٰٓ
إِلَٰهِ مُوسَىٰ وَإِنِّي لَأَظُنُّهُۥ كَٰذِبٗاۚ وَكَذَٰلِكَ زُيِّنَ لِفِرۡعَوۡنَ سُوٓءُ عَمَلِهِۦ وَصُدَّ عَنِ ٱلسَّبِيلِۚ وَمَا
كَيۡدُ فِرۡعَوۡنَ إِلَّا فِي تَبَابٖ ﴿٣٧﴾

**36-37.** ፈርዖንም፦ ሃማን ሆይ፣ መንገዶችን እደርስ ዘንድ ረዥም ህንፃን ካብልኝ አለ። የሰማያትን መንገዶች እደርስ ዘንድ። ከዚያ ወደ ሙሳ አምላክ እመለከት ዘንድ እኔም ውሸታም ነው ብዬ እጠረጥረዋለሁ አለ። እንደዚሁም ለፈርዖን መጥፎ ስራው ተሸለመለት። ከቅኑ መንገድም ታገደ። የፈርዖንም ተንኮል በከሳራ ውስጥ እንጂ አይደለም።

وَقَالَ ٱلَّذِيٓ ءَامَنَ يَٰقَوۡمِ ٱتَّبِعُونِ أَهۡدِكُمۡ سَبِيلَ ٱلرَّشَادِ ﴿٣٨﴾ يَٰقَوۡمِ إِنَّمَا هَٰذِهِ ٱلۡحَيَوٰةُ
ٱلدُّنۡيَا مَتَٰعٞ وَإِنَّ ٱلۡأٓخِرَةَ هِيَ دَارُ ٱلۡقَرَارِ ﴿٣٩﴾ مَنۡ عَمِلَ سَيِّئَةٗ فَلَا يُجۡزَىٰٓ إِلَّا مِثۡلَهَاۖ وَمَنۡ
عَمِلَ صَٰلِحٗا مِّن ذَكَرٍ أَوۡ أُنثَىٰ وَهُوَ مُؤۡمِنٞ فَأُوْلَٰٓئِكَ يَدۡخُلُونَ ٱلۡجَنَّةَ يُرۡزَقُونَ فِيهَا بِغَيۡرِ
حِسَابٖ ﴿٤٠﴾ ۞ وَيَٰقَوۡمِ مَا لِيٓ أَدۡعُوكُمۡ إِلَى ٱلنَّجَوٰةِ وَتَدۡعُونَنِيٓ إِلَى ٱلنَّارِ ﴿٤١﴾ تَدۡعُونَنِي
لِأَكۡفُرَ بِٱللَّهِ وَأُشۡرِكَ بِهِۦ مَا لَيۡسَ لِي بِهِۦ عِلۡمٞ وَأَنَا۠ أَدۡعُوكُمۡ إِلَى ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡغَفَّٰرِ ﴿٤٢﴾

**38-42.** ያም በአላህ ያመነው አለ፡- ወገኖቼ ሆይ፣ ተከተሉኝ ቀጥታውን መንገድ እመራችኋለሁና። ወገኖቼ ሆይ፣ ይህች ቅርቢቱ ሕይወት የጥቂት ቀናት መጣቀሚያ ብቻ ናት፤ መጨረሻይቱ ዓለም ግን እርሷ ትክክለኛና መርጊያ አገር ናት። መጥፎን የሰራ ሰው ብጤዋን እንጅ አይመነዳም። እርሱ ምዕመን ሆኖ ከወንድ ወይም ከሴት በጎን የሰራም ሰው እነዚያ ገነትን ይገባሉ። በእርሷ ውስጥ ያለ ቁጥጥር ይመገባሉ። ወገኖቼ ሆይ! ወደ መዳን የምጠራችሁ ስሆን ወደ እሳትም የምትጠሩኝ ስትሆኑ ለእኔ ምን አለኝ! በአላህ ልክድና በእርሱም ለእኔ እውቀት የሌለኝ ነገር በእርሱ እንዳጋራ ትጠሩኛላችሁ፤ እኔ አሸናፊና መሀሪ ወደ ሆነው አላህ እጠራችኋለሁ።

**ከመሃሪው ምዕራፉ ከአንቀፅ (18-42) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቂያማ ቀን ጭንቅ ምን ያህል እንደሚከብድ፤
2. ለግፈኞች የቂያማ ቀን ምንም ዘመድና ወዳጅ እንደማይኖር፤
3. የአላህ እውቀት ሰፊ ስለመሆኑ፤
4. የአላህ ውሳኔ ትክክለኛ ፍርዱ ተፈፃሚ እንደሚሆን፤
5. አዋቂ ማለት በሌላው የሚማር ነው የተባለውን ምሳሌያዊ አነጋገር ማፅደቅ፤
6. በወንጀሎች መቀጣት የተለመደ የአላህ ህግ ስለመሆኑ፤
7. አላህ ሊቀጣ የፈለገውን ማንም ሊያድነው እንደማይችል፤
8. ነብዩን (ﷺ) ማፅናት፤
9. በየጊዜው ያሉ ግፈኞች ንፁሃንን በሀሰት ከመወንጀል ወደ ኋላ እንደማይሉ፤
10. በግድያ ማስፈራራት የግፈኞች ልምድ እንደሆነ፤
11. ለተቸገረ ሁሉ ብቸኛ መጠጊያ አላህ ብቻ ስለመሆኑ
12. ጠንካራ እምነት የእውቀት ምንጭ፤
13. ያለፉትን ህዝቦች ታሪክ በማንሳት እንድንማር ማድረግ፤
14. ያለ እውቀት መከራከር ክልክል ስለመሆኑ፤
15. የትዕቢተኞችና የኩሩዎች መጨረሻ አስከፊነት፤
16. የአኼራ ቅጣትና ከቂያማ ቀን ጭንቀት ራስን ማዳን፤
17. ከመጠራጠርና ከማባከን መጠንቀቅ፤
18. ጠንካራ እምነት የእውቀት ምንጭ ስለመሆኑ፤
19. ያለፉትን ህዝቦች ታሪክ በማንሳት እንድንማር ማድረግ፤
20. የትዕቢተኞችና የኩሩዎችምንነት፤
21. ከመጠራጠርና ከማባከን ማስጠንቀቅ፤
22. መጥፎ ተግባራትን ከማስዋብ ማስጠንቀቅ፤
23. ከአኺራ ዘንግቶ በዚህች ዓለም ከመታለልና ከመሸንገል ማስጠንቀቅ፤
24. ከሞት በኋላ ለሂሳብ መቅረብ እንዳለ ማስጠንቀቅን እንማራለን፤

لَا جَرَمَ أَنَّمَا تَدْعُونَنِيٓ إِلَيْهِ لَيْسَ لَهُۥ دَعْوَةٌ فِي ٱلدُّنْيَا وَلَا فِي ٱلْـَٔاخِرَةِ وَأَنَّ مَرَدَّنَآ إِلَى ٱللَّهِ
وَأَنَّ ٱلْمُسْرِفِينَ هُمْ أَصْحَٰبُ ٱلنَّارِ ٤٣ فَسَتَذْكُرُونَ مَآ أَقُولُ لَكُمْۚ وَأُفَوِّضُ أَمْرِيٓ إِلَى ٱللَّهِۚ
إِنَّ ٱللَّهَ بَصِيرُۢ بِٱلْعِبَادِ ٤٤

**43-44.** በእርግጥ ወደ እርሱ የምትጠሩኝ ጣዖት ለእርሱ በቅርቢቱም ሆነ በመጨረሻይቱ ዓለም ተሰሚ ጥሪ የለውም መመለሻችንም እርግጥ ወደ አላህ ብቻ ነው። ወሰን አላፊዎችም እነርሱ የእሳት ጓዶች ናቸው። ወደ ፊትም ለእናንተ የምላችሁን ምክር ቅጣትን በምታዩ ጊዜ ታስታውሳላችሁ። ነገሬን ሁሉ ወደ አላህ አስጠጋለሁ። አላህ ባሮቹን ተመልካች ነውና።

فَوَقَىٰهُ ٱللَّهُ سَيِّـَٔاتِ مَا مَكَرُواْۖ وَحَاقَ بِـَٔالِ فِرْعَوْنَ سُوٓءُ ٱلْعَذَابِ ٤٥ ٱلنَّارُ يُعْرَضُونَ
عَلَيْهَا غُدُوّٗا وَعَشِيّٗاۚ وَيَوْمَ تَقُومُ ٱلسَّاعَةُ أَدْخِلُوٓاْ ءَالَ فِرْعَوْنَ أَشَدَّ ٱلْعَذَابِ ٤٦ وَإِذْ
يَتَحَآجُّونَ فِي ٱلنَّارِ فَيَقُولُ ٱلضُّعَفَٰٓؤُاْ لِلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُوٓاْ إِنَّا كُنَّا لَكُمْ تَبَعٗا فَهَلْ أَنتُم
مُّغْنُونَ عَنَّا نَصِيبٗا مِّنَ ٱلنَّارِ ٤٧ قَالَ ٱلَّذِينَ ٱسْتَكْبَرُوٓاْ إِنَّا كُلّٞ فِيهَآ إِنَّ ٱللَّهَ قَدْ حَكَمَ
بَيْنَ ٱلْعِبَادِ ٤٨ وَقَالَ ٱلَّذِينَ فِي ٱلنَّارِ لِخَزَنَةِ جَهَنَّمَ ٱدْعُواْ رَبَّكُمْ يُخَفِّفْ عَنَّا يَوْمٗا مِّنَ
ٱلْعَذَابِ ٤٩ قَالُوٓاْ أَوَلَمْ تَكُ تَأْتِيكُمْ رُسُلُكُم بِٱلْبَيِّنَٰتِۖ قَالُواْ بَلَىٰۚ قَالُواْ فَٱدْعُواْۗ وَمَا
دُعَٰٓؤُاْ ٱلْكَٰفِرِينَ إِلَّا فِي ضَلَٰلٍ ٥٠

**45-50.** ከመከሩዋቸውም መጥፎዎች አላህ ጠበቀው በፈርዖን ቤተሰቦችም ላይ ክፉ ቅጣት ሰፈረባቸው። እሳት በጧትና በማታ በእርሷ ላይ ይቀርባሉ። ሰዓቲቱም በምትሆንበት ቀን የፈርዖን ቤተሰቦች ብርቱን ቅጣት ገሀነምን አግቡዋቸው ይባላል። በእሳት ውስጥ የሚከራከሩበትን ጊዜ (አስታውስ) ደካማዎቹም ለነዚያ ለኮሩት እኛ ለእናንተ ተከታዮች ነበርንና እናንተ አሁን ከእሳት ከፊሉን ከእኛ ላይ ገፍታሪዎች ናችሁን? ይላሉ። እነዚያም የኮሩት እኛ ሁላችንም በውስጧ ነን አላህ በባሮቹ መካከል በእርግጥ ፈረደ ይላሉ። እነዚያም በእሳት ውስጥ ያሉት ለገሀነም ዘበኞች ጌታችሁን ለምኑልን ከእኛ በላይ ከቅጣቱ አንድን ቀን ያቃልልን ይላሉ። ዘበኞቹም መልዕክተኞቻችሁ በታምራቶች ይመጡላችሁ አልነበሩምን? ይላሉ ከሓዲዎችም እንዴታ መጥተውናል። እንጅ ግን አሰተባበልናቸው። ይላሉ እንግዲያውስ ፀልዩ የከሓዲያንም ፀሎት በከንቱ እንጂ አይደለም ይሏቸዋል።

إِنَّا لَنَنصُرُ رُسُلَنَا وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَيَوۡمَ يَقُومُ ٱلۡأَشۡهَٰدُ ﴿٥١﴾ يَوۡمَ لَا يَنفَعُ ٱلظَّٰلِمِينَ مَعۡذِرَتُهُمۡۖ وَلَهُمُ ٱللَّعۡنَةُ وَلَهُمۡ سُوٓءُ ٱلدَّارِ ﴿٥٢﴾

51-52. እኛ መልክተኞቻችንን እነዚያንም ያመኑትን በቅርቢቱ ሕይወት ምስክሮችንም በሚቆሙበት ቀን በእርግጥ እንረዳለን። በደለኞችን ምክንያታቸው በማይጠቅማቸው ቀን (እንረዳለን) ለነርሱም ርግማን አላቸው። ለነርሱም መጥፎ አገር አላቸው።

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا مُوسَى ٱلۡهُدَىٰ وَأَوۡرَثۡنَا بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱلۡكِتَٰبَ ﴿٥٣﴾ هُدٗى وَذِكۡرَىٰ لِأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ﴿٥٤﴾

53-54. ሙሳንም መምሪያ በእርግጥ ሰጠነው። የኢስራኤልንም ልጆች መጽሐፍን አወረስናቸው። ለባለ አእምሮዎች መሪና ገሰጭ ሲሆን።

فَٱصۡبِرۡ إِنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لِذَنۢبِكَ وَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ بِٱلۡعَشِيِّ وَٱلۡإِبۡكَٰرِ ﴿٥٥﴾

55. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ታገስም የአላህ ተስፋ እውነት ነውና፤ ለስህተትህም ምህረትን ለምን፤ ከቀትር በኋላም በማለዳም ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُجَٰدِلُونَ فِيٓ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ بِغَيۡرِ سُلۡطَٰنٍ أَتَىٰهُمۡ إِن فِي صُدُورِهِمۡ إِلَّا كِبۡرٞ مَّا هُم بِبَٰلِغِيهِۚ فَٱسۡتَعِذۡ بِٱللَّهِۖ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ ﴿٥٦﴾

56. እነዚያ የመጣላቸው አስረጅ ሳይኖር በአላህ አንቀፆች የሚከራከሩ በልቦቻቸው ውስጥ እነርሱ ደራሾች ያልሆኑት ኩራት ብቻ እንጂ ምንም የለም በአላህም ተጠበቅ፤ እነሆ እርሱ ሰሚና ተመልካች ነውና።

لَخَلۡقُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ أَكۡبَرُ مِنۡ خَلۡقِ ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٥٧﴾

57. ሰማያትንና ምድርን መፍጠር ሰዎችን ከመፍጠር ይልቅ ታላቅ ነው፤ ግን አብዛሀኞች ሰዎች አያውቁም።*

* ከመሃሪው ምዕራፍ ከ (56-57) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡-
አይሁዶች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ስለ ደጃል አንስተው ከእኛ ነው በመጨረሻው ዓለም ጊዜ የሚሆነው በማለት ጉዳዩን አካብደው እንዲህም እንዲህም ይሰራል ሲሉ አላህ ይህን አንቀፅ በማውረድ ነብዩ (ﷺ) ከደጃል ተንኮል እንዲጠበቁ አዘዛቸው። (ሱዩጢ።)

**ከመሃሪው ምዕራፉ ከአንቀፅ (41-57) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከእሳት ለመውጣት ጥሪ በሚያደርግና ወደ እሳት ጥሪ በሚያደርግ መካከል ያለውን ልዩነት መግለፅ፤
2. በሁሉ ነገር ላይ አባካኝ ከመሆን ማስጠንቀቅ፤
3. የቀብር ቅጣትና ደስታ እንዳለ ማረጋገጥ፤
4. የገሀነም ሰዎች እንደሚከራከሩ ማስተማር፤
5. ኩራትን ማውገዝ፤
6. በዱንያም ሆነ በአኼራ የከሃዲ ልመና ተቀባይነት እንደሌለው፤
7. የቂያማ ዕለት ምንም ምክንያት ቢቀርብ ተቀባይነት እንደሌለው፤
8. በእሳት ውስጥ ሆኖ የሚደረግ ዱዓ ተቀባይነት እንደሌለው፤
9. አላህ ለነብያትና ምእመናን እነሱን አንግሶ ጠላቶቻቸውን አርክሶና አጥፍቶ እንደሚያሳያቸው የገባውን ቃል፤
10. አላህ ለነብዩ ሙሳና ለበኒኢስራኤል የገባው ቃል በነብዩና (ﷺ) በሕዝቦቻቸው ሲደገም፤
11. ትዕግስት ማድረግ ግዴታ ስለመሆኑና በሰላት በዚክር መርካት፤
12. እውነትን በውሸት (ሐሰት) የሚከራከር ሁሉ ለራሱ ጥቅምምና ፍላጎት የሚሮጥ ትዕቢተኛ ስለመሆኑ፤
13. በሎጂክ ብቻ እንኳን የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ እንደሚቻል እንማራለን።

وَمَا يَسْتَوِي ٱلْأَعْمَىٰ وَٱلْبَصِيرُ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَلَا ٱلْمُسِيٓءُۚ قَلِيلًا مَّا
تَتَذَكَّرُونَ ﴿٥٨﴾ إِنَّ ٱلسَّاعَةَ لَءَاتِيَةٌ لَّا رَيْبَ فِيهَا وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يُؤْمِنُونَ ﴿٥٩﴾

**58-59.** እውርና የሚያይ እነዚያም አምነው መልካሞችን የሰሩትና መጥፎ ሰሪው አይስተካከሉም በጣም ጥቂትን ብቻ ትገስፃላችሁ። ሰዓቲቱ በእርግጥ መጪ ናት። በእርሷ ጥርጥር የለም። ግን አብዛሀኞቹ ሰዎች አያምኑም።

وَقَالَ رَبُّكُمُ ٱدْعُونِيٓ أَسْتَجِبْ لَكُمْۚ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَسْتَكْبِرُونَ عَنْ عِبَادَتِي سَيَدْخُلُونَ
جَهَنَّمَ دَاخِرِينَ ﴿٦٠﴾

**60.** ባሮቼ ሆይ፣ ጌታችሁ አለ። ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና። እነዚያ እኔን ከመገዛት የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነም በእርግጥ ይገባሉ።

ٱللَّهُ ٱلَّذِي جَعَلَ لَكُمُ ٱلَّيْلَ لِتَسْكُنُواْ فِيهِ وَٱلنَّهَارَ مُبْصِرًاۚ إِنَّ ٱللَّهَ لَذُو فَضْلٍ عَلَى
ٱلنَّاسِ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَشْكُرُونَ ﴿٦١﴾ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ خَٰلِقُ كُلِّ شَيْءٍ
لَّآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ فَأَنَّىٰ تُؤْفَكُونَ ﴿٦٢﴾ كَذَٰلِكَ يُؤْفَكُ ٱلَّذِينَ كَانُواْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ يَجْحَدُونَ ﴿٦٣﴾

**61-63.** አላህ ያ ለእናንተ ሌሊትን በውስጡ ልታርፉበት ጨለማ፤ ቀንንም (ልትሰሩበት) የሚያሳይ ብርሃን ያደረገላችሁ ነው። አላህ በሰዎች ላይ በእርግጥ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነውና። ግን አብዛሀኞቹ ሰዎች አያመሰግኑም። ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው። የነገሩ ሁሉ ፈጣሪ ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም። ታዲያ ከእምነት ወዴት ትመለሳላችሁ። እንደዚሁ እነዚያ በአላህ አንቀፆች ይክዱ የነበሩት ከእምነት ይመለሳሉ።

ٱللَّهُ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلْأَرْضَ قَرَارًا وَٱلسَّمَآءَ بِنَآءً وَصَوَّرَكُمْ فَأَحْسَنَ صُوَرَكُمْ وَرَزَقَكُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبُّكُمْ فَتَبَارَكَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٤﴾

**64.** አላህ ያ ምድርን መርጊያ ሰማይንም ጣሪያ ያደረገላቸሁ ነው። የተቀረፃችሁም ቅርፃችሁም ያሳመረ ከጣፋጮችም ሲሳዩች የሰጣችሁ ነው። ይሃችሁ ጌታችሁ አላህ ነው የዓለማትም ጌታ አላህ ላቀ።

هُوَ ٱلْحَىُّ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَٱدْعُوهُ مُخْلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ ٱلْحَمْدُ لِلَّهِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٥﴾

**65.** እርሱ ብቻ ሁል ጊዜ ህያው ነው። ከእርሱ ሌላ አምላክ የለም፤ ሃይማኖትንም ለርሱ የጠራችሁ ስትሆኑ ምስጋና ሁሉ ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ ብቻ ይገባው» የምትሉ ሆናችሁ ተገዙት።

۞قُلْ إِنِّى نُهِيتُ أَنْ أَعْبُدَ ٱلَّذِينَ تَدْعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ لَمَّا جَآءَنِىَ ٱلْبَيِّنَٰتُ مِن رَّبِّى وَأُمِرْتُ أَنْ أُسْلِمَ لِرَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٦٦﴾

**66.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ ከጌታዬ አስረጂዎች በመጡልኝ ጊዜ እነዚያን ከአላህ ሌላ የምትገዙዋቸውን እንዳልገዛ ተከልክያለሁ፤ ለዓለማትም ጌታም እንደገዛ ታዝዣለሁ በላቸው።

هُوَ ٱلَّذِى خَلَقَكُم مِّن تُرَابٍ ثُمَّ مِن نُّطْفَةٍ ثُمَّ مِنْ عَلَقَةٍ ثُمَّ يُخْرِجُكُمْ طِفْلًا ثُمَّ لِتَبْلُغُوٓا۟ أَشُدَّكُمْ ثُمَّ لِتَكُونُوا۟ شُيُوخًا وَمِنكُم مَّن يُتَوَفَّىٰ مِن قَبْلُ وَلِتَبْلُغُوٓا۟ أَجَلًا مُّسَمًّى وَلَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ﴿٦٧﴾

**67.** (ሰዎች ሆይ)፣ እርሱ ያ፣ ከዐፈር ከዚያም ከፍትወት ጠብታ ከዚያም ከረጋ ደም የፈጣራችሁ ነው። ከዚያም ህፃን አድርጎ ያወጣችኋል። ከዚያም ጥንካሪያችሁን ትደርሱ ዘንድ ከዚያም ሽማግሌ ትሆኑ ዘንድ ያቆያችኋል።

ከናንተም ውስጥ ከዚህ በፊት የሚሞት አለ። ይህንንም ያደረገው ልትኖሩና የተወሰነ ጊዜም ልትደርሱ ታውቁም ዘንድ ነው።

هُوَ ٱلَّذِى يُحْيِۦ وَيُمِيتُ ۖ فَإِذَا قَضَىٰٓ أَمْرًا فَإِنَّمَا يَقُولُ لَهُۥ كُن فَيَكُونُ ﴿٦٨﴾

68. እርሱ ያ ህያው የሚያደርግ የሚያሞትም ነው። አንዳችን ነገር በሻም ጊዜ ለእርሱ የሚለው ሁን ነው ወዲያውም ይሆናል።

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ يُجَٰدِلُونَ فِىٓ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ أَنَّىٰ يُصْرَفُونَ ﴿٦٩﴾ ٱلَّذِينَ كَذَّبُوا۟ بِٱلْكِتَٰبِ وَبِمَآ
أَرْسَلْنَا بِهِۦ رُسُلَنَا ۖ فَسَوْفَ يَعْلَمُونَ ﴿٧٠﴾ إِذِ ٱلْأَغْلَٰلُ فِىٓ أَعْنَٰقِهِمْ وَٱلسَّلَٰسِلُ يُسْحَبُونَ ﴿٧١﴾
فِى ٱلْحَمِيمِ ثُمَّ فِى ٱلنَّارِ يُسْجَرُونَ ﴿٧٢﴾ ثُمَّ قِيلَ لَهُمْ أَيْنَ مَا كُنتُمْ تُشْرِكُونَ ﴿٧٣﴾ مِن دُونِ
ٱللَّهِ ۖ قَالُوا۟ ضَلُّوا۟ عَنَّا بَل لَّمْ نَكُن نَّدْعُوا۟ مِن قَبْلُ شَيْـًٔا ۚ كَذَٰلِكَ يُضِلُّ ٱللَّهُ ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٧٤﴾
ذَٰلِكُم بِمَا كُنتُمْ تَفْرَحُونَ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ وَبِمَا كُنتُمْ تَمْرَحُونَ ﴿٧٥﴾ ٱدْخُلُوٓا۟ أَبْوَٰبَ
جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَا ۖ فَبِئْسَ مَثْوَى ٱلْمُتَكَبِّرِينَ ﴿٧٦﴾

69-76. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደነዚያ በአላህ አንቀፆች ወደሚከራከሩት ከእምነት እንዴት እንደሚመለሱ አታይምን? ወደ እነዚያ በመጽሐፉ በዚያም መልዕክተኞቻችንን በእርሱ በላክንበት ወዳስተባበሉበት አታይምን? ወደፊትም ያውቃሉ። እንዘዝላዎቹና ሰንሰለቶች በአንገቶቻቸው ላይ በተደረጉ ጊዜ (በእርሷ) ይጎተታሉ በገሀነም ውስጥ (ይጎተታሉ)። ከዚያም በእሳት ውስጥ ይማገዳሉ። ከዚያም ለእነርሱ ይባላሉ:- (በአላህ) ታጋሯቸው የነበራችሁት የታሉ? ከአላህ ሌላ የምታጋሩዋቸው ከእኛ ተሰወሩን ከቶ ከዚህ በፊት ምንም የምንገዛ አልነበርንም ይላሉ። ልክ እንደዚሁ አላህ ካሐዲያንን ያሳስታል። ይህ (ቅጣታችሁ) ያላአግባብ በምድር ውስጥ ትደሰቱ በነበራችሁትና ትንበጣረሩ በነበራችሁት ነው ይባላሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የገሀነምን በሮች ውስጧ ዘወታሪዎች ስትሆኑ ግቡ (ይባላሉ)፤ የትዕቢተኞችም መኖሪያ (ገሀነም) ምን ትከፋ!

فَٱصْبِرْ إِنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّ ۚ فَإِمَّا نُرِيَنَّكَ بَعْضَ ٱلَّذِى نَعِدُهُمْ أَوْ نَتَوَفَّيَنَّكَ فَإِلَيْنَا
يُرْجَعُونَ ﴿٧٧﴾ وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا رُسُلًا مِّن قَبْلِكَ مِنْهُم مَّن قَصَصْنَا عَلَيْكَ وَمِنْهُم مَّن لَّمْ
نَقْصُصْ عَلَيْكَ ۗ وَمَا كَانَ لِرَسُولٍ أَن يَأْتِىَ بِـَٔايَةٍ إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ فَإِذَا جَآءَ أَمْرُ ٱللَّهِ قُضِىَ
بِٱلْحَقِّ وَخَسِرَ هُنَالِكَ ٱلْمُبْطِلُونَ ﴿٧٨﴾

77-78. ታገስም የአላህ ቀጠሮ እውነት ነውና፤ የዚያንም የምናስፈራራቸውን ከፊሉን በህይወትህ ብናሳይህ (መልካም ነው) ወይም ብንገድልህ ወደ እኛ ይመለሳሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊትም መልዕክተኞችን በእርግጥ ልከናል ከእነርሱ በአንተ ላይ የተረክንልህ አለ። ከእነርሱም ባንተ ላይ ያልተረክነው አለ። ለማንኛውም መልዕክተኛ በአላህ ፈቃድ ካልሆነ ታዐምርን ሊያመጣ አይገባውም። የአላህም ትዕዛዝ በመጣ ጊዜ በእውነት ይፈረዳል። እዚያ ዘንድም አጥፊዎች ይከስራሉ።

ٱللَّهُ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلْأَنْعَٰمَ لِتَرْكَبُوا۟ مِنْهَا وَمِنْهَا تَأْكُلُونَ ﴿٧٩﴾ وَلَكُمْ فِيهَا مَنَٰفِعُ وَلِتَبْلُغُوا۟ عَلَيْهَا حَاجَةً فِى صُدُورِكُمْ وَعَلَيْهَا وَعَلَى ٱلْفُلْكِ تُحْمَلُونَ ﴿٨٠﴾ وَيُرِيكُمْ ءَايَٰتِهِۦ فَأَىَّ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ تُنكِرُونَ ﴿٨١﴾

79-81. አላህ ያ፣ ለእናንተ ግመልን ከብትንና ፍየልን ከእርሷ ከፊሏን ልትጋልቡ የፈጠረላችሁ ነው። ከእርሷም ትበላላችሁ። ለእናንተም በርሷ ውስጥ ጥቅሞች አሏችሁ። በእርሷም ላይ ዕቃን በመጫን በልቦቻችሁ ያሰባችሁትን ጉዳይ ትደርሱ ዘንድ ፈጠረላችሁ በእርሷም ላይ በመርከቦችም ላይ ትሳፈራላችሁ። ታዐምራቶችንም ያሳያችኋል። ታዲያ ከአላህ ታምራት የትኛውን ትክዳላችሁ?

أَفَلَمْ يَسِيرُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ فَيَنظُرُوا۟ كَيْفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ ۚ كَانُوٓا۟ أَكْثَرَ مِنْهُمْ وَأَشَدَّ قُوَّةً وَءَاثَارًا فِى ٱلْأَرْضِ فَمَآ أَغْنَىٰ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَكْسِبُونَ ﴿٨٢﴾ فَلَمَّا جَآءَتْهُمْ رُسُلُهُم بِٱلْبَيِّنَٰتِ فَرِحُوا۟ بِمَا عِندَهُم مِّنَ ٱلْعِلْمِ وَحَاقَ بِهِم مَّا كَانُوا۟ بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿٨٣﴾ فَلَمَّا رَأَوْا۟ بَأْسَنَا قَالُوٓا۟ ءَامَنَّا بِٱللَّهِ وَحْدَهُۥ وَكَفَرْنَا بِمَا كُنَّا بِهِۦ مُشْرِكِينَ ﴿٨٤﴾ فَلَمْ يَكُ يَنفَعُهُمْ إِيمَٰنُهُمْ لَمَّا رَأَوْا۟ بَأْسَنَا ۖ سُنَّتَ ٱللَّهِ ٱلَّتِى قَدْ خَلَتْ فِى عِبَادِهِۦ ۖ وَخَسِرَ هُنَالِكَ ٱلْكَٰفِرُونَ ﴿٨٥﴾

82-85. የእነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ህዝቦች ፍፃሜ እንዴት እንደነበር ይመለከቱ ዘንድ በምድር ላይ አይሄዱምን? ከእነርሱ ይበልጥ ብዙዎች በኃይልና በምድር ላይ በተዋቸው ምልክቶችም በጣም ብርቱዎች ነበሩ። ያም ይሰሩት የነበሩት ከእነርሱ ምንም አልጠቀማቸውም። መልዕክቶቻቸውም ታምራቶችን ባመጡላችሁ ጊዜ እነርሱ ዘንድ ባለው ዕውቀት ተደሰቱ። በእርሱ ይሳለቁበት የነበሩት ቅጣትም በእነርሱ ላይ ሰፈረባቸው። ብርቱ ቅጣታችንንም ባዩ ጊዜ በአላህ አንድ ሲሆን አምነናል በርሱም እናጋራ በነበርነው ጣዖታት ከደናል አሉ። ብርቱ ቅጣታችንን ባዩ ጊዜ ማመናቸውም የሚጠቅማቸው

አልነበረም። የአላህን ደንብ ያችን በባሮቹ ውስጥ ያለፈችውን ተጠንቀቁ። በዚያ ጊዜም ከሓዲያን ከሰሩ።

**ከመሃሪው ምዕራፉ ከአንቀፅ (58-85) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሁለት ተቃራኒ ነገሮች በአንድ ላይ መሰብሰብ እንደማይቻል፤
2. የትንሳኤ ዕለት መቅረቧን የሚያመላክቱ ማስረጃዎች መኖራቸውን፤
3. ስለ ዱዓ አስፈላጊነትና ተቀባይነት እንዲኖረው መሟላት ስለሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች በሰፊው ማብራሪያ መስጠት፤
4. ዱዓ የማያደርጉ ሰዎች በአላህ ዘንድ የሚጠብቃቸው ከፍተኛ ውርደት እንደሆነ፤
5. አላህ ለህዝቦች የዋላቸውን ውለታዎች፤
6. የአላህን ኃያልነት የሚያመላክቱ ክንውኖችን ማውሳት፤
7. ተውሒድን ማስተማር የሰው ልጅ የአፈጣጠርንና እድገት ሂደቱን ማየት፤
8. በአላህ አናቅፅ ከሚያስተባብሉ ሰዎች ተግባር መገረም፤
9. እውነትን ሲያወግዙ የኑሮ ከሓዲያን በገሀነም እሳት ውስጥ እንዴት እንደሚንገላቱ፤
10. ከአላህ ኒዕማ ሌላ በሆነ ነገር ከመደሰት ማስጠንቀቅ ኩራትን ማውገዝ፤
11. በዳዕዋ ስራ ላይ ለሚከሰቱ ልዩ ልዩ ችግሮች ትዕግስት ማድረግ አስፈላጊና ግዴታም ስለመሆኑ፤
12. ተዓምራት በአላህ ፈቃድ እንጂ ለማንም እንደማይገኝ፤
13. ከነብያት ታሪካቸው ያልተነገሩና ጭራሽ ያልተወሱ ሰዎች እንዳሉ፤
14. አላህ ለሰዎች ከዋለላቸው ውለታዎች በጥቂቱሁለት ተቃራኒ ነገሮች በአንድ ላይ መሰብሰብ እንደማይቻል፤
15. አላህ ለሰዎች ከዋለላቸው ውለታዎች በጥቂቱ፤
16. በየሀገሩ በመዞር መማር ተገቢ ስለመሆኑ፤
17. በማቴሪያል ኃይል ብቻ ከምንም መከላከል እንደማይቻል፤
18. ማቴሪያሊስቶች በእውቀታቸው እንደሚኮሩ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የመሃሪው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (41)
# የተብራራችው ምዕራፍ
## (ሱረቱ ፋሲለት)

سُورَةُ فُصِّلَتْ

**(በመካ የወረደ ምዕራፍ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (54) ናቸው።**
**የሱረቱ ፉስ-ሲለት መግቢያ**

ፍጥረተ-ዓለም መጀመሪያ እንደጭስ ዳመና እንደነበር ቁርኣን (ሱራ-ፉሲለት አያት 11) ላይና ሰማይና መሬት በአንድ ተያይዘው የነበሩ ሲሆን ከጊዜ በኋላ የተለያዩ መሆናቸውን ቁርኣን (ሱራ, አል-አንቢያ አያት 30) ላይ ከ (1400) አመት በፊት የገለፀውን ሳንይስ የደረሰበት በቅርቡ ነበር። አይገርምም! ዶ ር ልፉርድ የተባለው የጅኦሎጅ ፕሮፌሰር ሙሐመድ ከየት እንደመጣ ብናስብ በኔ አመለካከት ፍጥረተ ዓለሞች ከአንድ ምንጭ መምጣታቸውን ሲሉ (ሙሐመድ) ከራሱ አእምሮ ስለ ኒውክለር ፊዚክስ በዚያን ዘመን ይናገራል ብዬ አልገምትም። ምክንያቱም ሳይንስ እነዚህን ነገሮች በተራቀቀ መሳሪያ በመታገዝ ያረጋገጠው በቅርቡ ነውና። ከ (60) አ . ል በፊት ስለ-ፍጥረተ ዓለም (ዩንቨርስ) እንደጭስ ዳመና እንደነበር ዩኒቨርስቲዎች ማህበር የአስትሮኖሚ (ስነ-ከዋክብት ምርምር) ጥናት አረጋግጧል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

حمٓ ۝١

**1.** ሓ፤ ሚይም፤*

✶ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፤ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

تَنزِيلٌ مِّنَ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ ۝٢ كِتَٰبٌ فُصِّلَتۡ ءَايَٰتُهُۥ قُرۡءَانًا عَرَبِيًّا لِّقَوۡمٍ يَعۡلَمُونَ ۝٣
بَشِيرًا وَنَذِيرًا فَأَعۡرَضَ أَكۡثَرُهُمۡ فَهُمۡ لَا يَسۡمَعُونَ ۝٤ وَقَالُواْ قُلُوبُنَا فِيٓ أَكِنَّةٍ مِّمَّا
تَدۡعُونَآ إِلَيۡهِ وَفِيٓ ءَاذَانِنَا وَقۡرٌ وَمِنۢ بَيۡنِنَا وَبَيۡنِكَ حِجَابٌ فَٱعۡمَلۡ إِنَّنَا عَٰمِلُونَ ۝٥

**2-5.** ይህ ቁርኣን እጅግ በጣም ሩህሩህና በጣም አዛኝ ከሆነው ጌታ ከአላህ የተወረደ ነው። አናቅጾቹ የተብራሩ የሆነ መጽሐፍ ነው። አረበኛ ቁርኣን ሲሆን ለማያውቁ ሕዝቦች (የተብራራ) ነው። አብሳሪና አስፈራሪ ሲሆን ተወረደ አብዛሀኞቻቸውም ተውት። እነርሱም አይሰሙም። አሉም፡- ልቦቻችን ከዚያ ወደርሱ ከምትጠራን እምነት በመሸፈኛዎች ውስጥ ናቸው። በጆሮቻችንም ላይ ድንቁርና አለ። በእኛና በእናንተ መካከል ግርዶሽ አለ። በሃይማኖትህ ስራ እኛ ሰሪዎች ነንና።

قُلْ إِنَّمَآ أَنَا۠ بَشَرٌ مِّثْلُكُمْ يُوحَىٰٓ إِلَىَّ أَنَّمَآ إِلَٰهُكُمْ إِلَٰهٌ وَٰحِدٌ فَٱسْتَقِيمُوٓا۟ إِلَيْهِ وَٱسْتَغْفِرُوهُ ۗ
وَوَيْلٌ لِّلْمُشْرِكِينَ ﴿٦﴾ ٱلَّذِينَ لَا يُؤْتُونَ ٱلزَّكَوٰةَ وَهُم بِٱلْءَاخِرَةِ هُمْ كَٰفِرُونَ ﴿٧﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ
ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمْ أَجْرٌ غَيْرُ مَمْنُونٍ ﴿٨﴾

**6-8.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እንዲህ በላቸው እኔ መሰላችሁ ሰው ብቻ ነኝ። አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነው። ወደ እርሱም ቀጥ በሉ። ምህረትንም ለምኑት ማለት ወደ እኔ ይወረድልኛል ለአጋሪዎችም ወዩላቸው ለእነዚያ ዘካን ለማይሰጡ እነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም እነርሱ ከሓዲዎች ለሆኑት (ወዩላቸው)። እነዚያ የዳኑትና በጎ ስራዎችን የሰሩት ለእነርሱ የማይቆረጥ ምንዳ አላቸው።

۞ قُلْ أَئِنَّكُمْ لَتَكْفُرُونَ بِٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْأَرْضَ فِى يَوْمَيْنِ وَتَجْعَلُونَ لَهُۥٓ أَندَادًا ۚ ذَٰلِكَ رَبُّ
ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٩﴾ وَجَعَلَ فِيهَا رَوَٰسِىَ مِن فَوْقِهَا وَبَٰرَكَ فِيهَا وَقَدَّرَ فِيهَآ أَقْوَٰتَهَا فِىٓ أَرْبَعَةِ أَيَّامٍ
سَوَآءً لِّلسَّآئِلِينَ ﴿١٠﴾ ثُمَّ ٱسْتَوَىٰٓ إِلَى ٱلسَّمَآءِ وَهِىَ دُخَانٌ فَقَالَ لَهَا وَلِلْأَرْضِ ٱئْتِيَا طَوْعًا
أَوْ كَرْهًا قَالَتَآ أَتَيْنَا طَآئِعِينَ ﴿١١﴾ فَقَضَىٰهُنَّ سَبْعَ سَمَٰوَاتٍ فِى يَوْمَيْنِ وَأَوْحَىٰ فِى كُلِّ سَمَآءٍ
أَمْرَهَا ۚ وَزَيَّنَّا ٱلسَّمَآءَ ٱلدُّنْيَا بِمَصَٰبِيحَ وَحِفْظًا ۚ ذَٰلِكَ تَقْدِيرُ ٱلْعَزِيزِ ٱلْعَلِيمِ ﴿١٢﴾

**9-12.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ በዚያ ምድርን በሁለት ቀኖች ውስጥ በፈጠረው አምላክ በእርግጥ ትክዳላችሁን? ለርሱም ባላንጣዎች ታደርጋላችሁን? ያ ይህንን የሰራው የዓለማት ጌታ ነው በላቸው። በርሷም ከበላይዋ የረጉ ጋራዎችን አደረገ። በእርሷም በረከትን አደረገ። በውስጧም ምግቦችዋን (ካለፉት ሁለት ቀኖች ጋር) በአራት ቀናት ውስጥ ለጠያቂዎች ትክክል ሲሆን ወሰነ። ከዚያ ወደ ሰማይ እርሷ ጭስ ሆና ሳለች አሰበ ለእርሷም ለምድርም ወዳችሁም ሆነ ወይም ጠልታችሁ ኑ አላቸው። ታዛዦች ሆነን መጣን አሉ። በሁለት ቀናትም ውስጥ ሰባት ሰማያት አደረጋቸው። በሰማይም ሁሉ ነገሯን አዘጋጀ። ቅርቢቱንም ሰማይ በመብራቶች አጌጥን ከሰይጣናት መጠበቅንም ጠበቅናት። ይህ የአሸናፊው፤ የአዋቂው ጌታ ውሳኔ ነው።

**ከተብራራው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-12) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አረብኛን ማወቅ የማንኛውም ሙስሊም ግዴታ ስለመሆኑ፤
2. ቁርአን የማብሰርና የማስፈራራት ስልትን እንደሚጠቀም፤
3. በየ ጊዜው ያሉ ከሓዲያን ለተውሒድና ለሙስሊሞች ያላቸው ብርቱ ጥላቻ፤
4. ተውሒድ ማስተማር፤

5. በአላህ ህግ መሰረት ቀጥ ማለት፤
6. በየትኛውም ወንጀል የአላህን ምህረት መጠየቅ ግዴታ ስለመሆኑ፤
7. የዘካ ግዳጅነት፤
8. ከክህደት የበለጠ ምንም ወንጀል እንደሌለ፤
9. አላህ ዓለምን የፈጠረበት ቀናት ማሳወቁ፤
10. ከከዋክብት ጥቅሞች መካከል፤
11. የሰማይ ጌጣ ጌጥ፤
12. ለሰይጣን ማቃጠያ መሆን እንደሆነ እንማራለን፤

فَإِنْ أَعْرَضُواْ فَقُلْ أَنذَرْتُكُمْ صَٰعِقَةً مِّثْلَ صَٰعِقَةِ عَادٍ وَثَمُودَ ﴿١٣﴾ إِذْ جَآءَتْهُمُ ٱلرُّسُلُ مِنۢ بَيْنِ أَيْدِيهِمْ وَمِنْ خَلْفِهِمْ أَلَّا تَعْبُدُوٓاْ إِلَّا ٱللَّهَۖ قَالُواْ لَوْ شَآءَ رَبُّنَا لَأَنزَلَ مَلَٰٓئِكَةً فَإِنَّا بِمَآ أُرْسِلْتُم بِهِۦ كَٰفِرُونَ ﴿١٤﴾

**13-14.** ከእምነት እምቢ ቢሉም እንደ ዓድና ሰሙድ መቅሰፍት ብጤ የሆነን መቅሰፍት አስጠነቅቃችኋለሁ በላቸው። መልዕክተኞች አላህን እንጂ ሌላን አትገዙ በማለት ከስተፊታቸውም ከበስተኋላቸውም በመጡላቸው ጊዜ ጌታችን በሻ ኖሮ መላዕክትን ባወረደ ነበር ስለዚህ እኛ በዚህ በእርሱ በተላካችሁት ከሓዲያን ነን አሉ።

فَأَمَّا عَادٌ فَٱسْتَكْبَرُواْ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ وَقَالُواْ مَنْ أَشَدُّ مِنَّا قُوَّةًۖ أَوَلَمْ يَرَوْاْ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِى خَلَقَهُمْ هُوَ أَشَدُّ مِنْهُمْ قُوَّةًۖ وَكَانُواْ بِـَٔايَٰتِنَا يَجْحَدُونَ ﴿١٥﴾ فَأَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ رِيحًا صَرْصَرًا فِىٓ أَيَّامٍ نَّحِسَاتٍ لِّنُذِيقَهُمْ عَذَابَ ٱلْخِزْىِ فِى ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَاۖ وَلَعَذَابُ ٱلْءَاخِرَةِ أَخْزَىٰۖ وَهُمْ لَا يُنصَرُونَ ﴿١٦﴾

**15-16.** ዓድም በምድር ላይ ያለ አግባብ ኮሩ፤ ከእኛ ይበልጥ በኃይል ብርቱ ማን ነው? አሉም ያ የፈጠራቸው አላህ እርሱ በኃይል ከእነርሱ ይበልጥ የበረታ መሆኑን አያምኑምን? በታምራታችንም ይክዱ ነበሩ። በቅርቢቱ ሕይወት የውርደትን ቅጣት ልናቀምሳቸውም በእሱ አላህ የሚንሻሻ ብርቱ ነፋስ መናጢዎች በሆኑ ቀናት ውስጥ ላክንባቸው። የመጨረሻይቱ ዓለም ስቃይ በጣም አዋራጅ ነው። እነርሱም አይረዱም።

وَأَمَّا ثَمُودُ فَهَدَيْنَٰهُمْ فَٱسْتَحَبُّواْ ٱلْعَمَىٰ عَلَى ٱلْهُدَىٰ فَأَخَذَتْهُمْ صَٰعِقَةُ ٱلْعَذَابِ ٱلْهُونِ بِمَا كَانُواْ يَكْسِبُونَ ﴿١٧﴾ وَنَجَّيْنَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَكَانُواْ يَتَّقُونَ ﴿١٨﴾

**17-18.** ሰሙዶችማ ወደ ቀናው መንገድ መራናቸው። እነርሱ ግን እውርነት ከቅንነት ላይ መረጡ። ይሰሩትም በነበሩት ኃጢአት አሳናሽ የሆነችው የመብረቅ ቅጣት ያዘቻቸው። እነዚያንም ያመኑትንና ይጠነቀቁ የነበሩትን አዳንናቸው።

وَيَوۡمَ يُحۡشَرُ أَعۡدَآءُ ٱللَّهِ إِلَى ٱلنَّارِ فَهُمۡ يُوزَعُونَ ١٩ حَتَّىٰٓ إِذَا مَا جَآءُوهَا شَهِدَ عَلَيۡهِمۡ سَمۡعُهُمۡ وَأَبۡصَٰرُهُمۡ وَجُلُودُهُم بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٢٠ وَقَالُواْ لِجُلُودِهِمۡ لِمَ شَهِدتُّمۡ عَلَيۡنَاۖ قَالُوٓاْ أَنطَقَنَا ٱللَّهُ ٱلَّذِيٓ أَنطَقَ كُلَّ شَيۡءٖۚ وَهُوَ خَلَقَكُمۡ أَوَّلَ مَرَّةٖ وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ٢١

**19-21.** የአላህም ጠላቶች ወደ እሳት የሚሰበሰቡበትን ቀን አስታውሱ። እነርሱም የሚከመከሙ ሆነው ይነዳሉ። በመጧትም ጊዜ ጆሮዎቻቸው ዓይኖቻቸውና ቆዳዎቻቸውም ይሰሩት በነበሩት በእነርሱ ላይ ይመሰክርባቸዋል። ለቆዳዎቻቸውም በእኛ ላይ ለምን መሰከሩብን ይላሉ፤ ያ አንዳቹን ነገር ሁሉ ያናገረው አላህ አናገረን እነርሱም በመጀመሪያ ጊዜ ፈጠራችሁ ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ ይሏቸዋል።

وَمَا كُنتُمۡ تَسۡتَتِرُونَ أَن يَشۡهَدَ عَلَيۡكُمۡ سَمۡعُكُمۡ وَلَآ أَبۡصَٰرُكُمۡ وَلَا جُلُودُكُمۡ وَلَٰكِن ظَنَنتُمۡ أَنَّ ٱللَّهَ لَا يَعۡلَمُ كَثِيرٗا مِّمَّا تَعۡمَلُونَ ٢٢ وَذَٰلِكُمۡ ظَنُّكُمُ ٱلَّذِي ظَنَنتُم بِرَبِّكُمۡ أَرۡدَىٰكُمۡ فَأَصۡبَحۡتُم مِّنَ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٢٣

**22-23.** ጆሮዎቻችሁ ዓይኖቻችሁና ቆዳዎቻችሁ በእናንተ ላይ ከመመስከራቸው የምትደበቁ አልነበራችሁም። ግን አላህ ከምትሰሩት ብዙውን አያውቅም ብላችሁ ጠረጠራችሁ። ይህም ለጌታችሁ የጠረጣችሁት ጥርጣሬያችሁ አጠፋችሁ ከከሳሪዎችም ሆናችሁ (ይባላሉ)።

ከተብራራው ምዕራፍ (22) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- (ሀ) አህመድ፤ ቡኻሪ፤ ሙስሊም፤ ቲርሚዚ፤ ነሳኢና ሌሎችም ኢብኑ መስዑድን ዋቢ አድርገው በዘገቡት ሐዲስ በካዕባ መጋረጃ ውስጥ ተደብቄ እያለሁ ሁለት ቁረይሾች ከአንድ ሰቂፍዊ አማቻቸው ጋር ወይም ሁለት ሰቂፋውያን ከአንድ ቀረይሽ አማቻቸው ጋር ከአንድ ቤት ውስጥ ሳሉ እርስ በርሳቸው አላህ አሁን የምናወራውን ሰምቷልን? በመባባል ሲጠያየቁ አንዱ ተነስቶ ግማሹን ሰምቷል ሲል ሌሎች ደግሞ ግማሹን ከሰማ ሁሉንም ይሰማናል ሲሉ ሌላው ደግሞ ድምፃችንን ከፍ ስናደርግ ይሰማናል ሲል ሌላው ደግሞ ድምፃችን ከፍ ያለበትን ከሰማን ዝቅ ያደረገንበትንም ይሰማል በማለት ሲወዛገቡ ሰምቼ ወደ ነብዩ ሄጄ ስነግራቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

(ለ) ሁለት የመካ ሰዎች ከአንድ ጧኢፍ ሰዎች የሆነ አማቻቸው ጋር ሁነው ሲያወሩ አንዱ ለሌላው አላህ ይሰማናል ብላችሁ ታምናላችሁ አለ። ሌላው ተነስቶ ግማሹን ይሰማናል አለ። ሌላው ተነስቶ ግማሹን ከሰማ ሙሉውን ይሰማናል። በማለቱ ነው። ይህ አንቀፅ የወረደበት።

(ሐ) ሁለት የመካ ሰዎች ከአንድ ጧኢፍ ሰዎች የሆነ አማቻቸው ጋር ሁነው ሲያወሩ አንዱ ለሌላው አላህ ይሰማናል ብላችሁ ታምናላችሁ አለ። ሌላው ተነስቶ ግማሹን ይሰማናል አለ። ሌላው ተነስቶ ግማሹን ከሰማ ሙሉውን ይሰማናል። በማለቱ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

فَإِن يَصْبِرُوا۟ فَٱلنَّارُ مَثْوًى لَّهُمْ ۖ وَإِن يَسْتَعْتِبُوا۟ فَمَا هُم مِّنَ ٱلْمُعْتَبِينَ ﴿٢٤﴾ ۞ وَقَيَّضْنَا لَهُمْ
قُرَنَآءَ فَزَيَّنُوا۟ لَهُم مَّا بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَمَا خَلْفَهُمْ وَحَقَّ عَلَيْهِمُ ٱلْقَوْلُ فِىٓ أُمَمٍ قَدْ خَلَتْ مِن
قَبْلِهِم مِّنَ ٱلْجِنِّ وَٱلْإِنسِ ۖ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ خَٰسِرِينَ ﴿٢٥﴾

**24-25.** ቢታገሱም እሳት ለእነርሱ መኖሪያቸው ናት፡፡ ወደ ሚወዱት መመለስንም ቢጠይቁ እነርሱ ተቀባይ የሚያገኙ አይደሉም፡፡ ለእነርሱም ቁራኛዎችን አዘጋጀንላቸው በፊታቸውን ያለውንና በኋላቸው ያለውንም ሁሉ ለእነርሱ ሸለሙላቸው ከአጋንንትና ከሰውም ከእነርሱ በፊት በእርግጥ ካለፉት ህዝቦች ጋር ሆነው ቃሉ በእነርሱ ላይ ተረጋገጠባቸው፡፡ እነርሱ በእርግጥ ከሳሪዎች ነበሩና፡፡

**ከተብራራው ምዕራፍ ከአንቀፅ (13-24) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የእውነት ጥሪ ካለመቀበል ከሚመጣው አደጋ ማስጠንቀቅ፤
2. ተውሒድን ማረጋገጥ፤
3. የነብያት ጥሪ አንድ መሆን፤
4. ከኩራት ማስጠንቀቅ፤
5. ችግር የሚፈጠረው በወንጀል ምክኒያት ስለመሆኑ፤
6. እምነትና አላህን መፍራት ከገሀነም ነጻ መውጫ ዋና መንገዶች መሆናቸው፤
7. የሙቶ መነሳትን ሐቅነት ማረጋጥ፤
8. ልዩ ልዩ ወንጀሎችን ከመስራት ማስጠንቀቅ፤
9. በአላህ ላይ መጥፎ ጥርጣሬ መከላከል፤
10. በአላህ መልካም ማሰብ እንዳለብን፤

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَا تَسْمَعُوا۟ لِهَٰذَا ٱلْقُرْءَانِ وَٱلْغَوْا۟ فِيهِ لَعَلَّكُمْ تَغْلِبُونَ ﴿٢٦﴾ فَلَنُذِيقَنَّ
ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ عَذَابًا شَدِيدًا وَلَنَجْزِيَنَّهُمْ أَسْوَأَ ٱلَّذِى كَانُوا۟ يَعْمَلُونَ ﴿٢٧﴾ ذَٰلِكَ جَزَآءُ
أَعْدَآءِ ٱللَّهِ ٱلنَّارُ ۖ لَهُمْ فِيهَا دَارُ ٱلْخُلْدِ ۖ جَزَآءًۢ بِمَا كَانُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا يَجْحَدُونَ ﴿٢٨﴾

**26-28.** እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች ይህንን ቁርኣን አታዳምጡ ታሸንፉም ዘንድ ሲነበብ በእሱ ውስጥ ተንጫጩ አሉ፡፡ እነዚያንም በአላህ የካዱ ሰዎች ብርቱን ቅጣት እናቀምሳቸዋለን፡፡ የዚያንም ይሰሩት የነበሩትን መጥፎውን ምንዳ እንመነዳቸዋለን፡፡ ይህ የአላህ ጠላቶች ፍዳ ነው፡፡ እሳት በውስጧ ለእነርሱ የዘላለም መኖሪያ አገር አላቸው፡፡ በአንቀጾቻችን ይክዱ በነበሩት ምንዳ ይመነዳሉ፡፡

ከተብራራው ምዕራፍ (27) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡- ኸባብ ኢብኑል አረትና መሰል ሱሀቦች ሐብትንና ምቾትን ተመኝተው ስለነበር ነው፡፡ ለእነሱ መልስ ይሆን ዘንድ የወረደው፡፡

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ رَبَّنَآ أَرِنَا ٱلَّذَيۡنِ أَضَلَّانَا مِنَ ٱلۡجِنِّ وَٱلۡإِنسِ نَجۡعَلۡهُمَا تَحۡتَ أَقۡدَامِنَا
لِيَكُونَا مِنَ ٱلۡأَسۡفَلِينَ ٢٩

**29.** እነዚያም የካዱት በእሳት ውስጥ ሆነው ጌታችን ሆይ! እነዚያ ከአጋንንትና ከሰው ያሳሳተንን አሳየን ከታችኞች ይሆኑ ዘንድ ከጫማዎቻችን ስር እናደርጋቸዋለንና ይላሉ።

إِنَّ ٱلَّذِينَ قَالُواْ رَبُّنَا ٱللَّهُ ثُمَّ ٱسۡتَقَٰمُواْ تَتَنَزَّلُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ أَلَّا تَخَافُواْ وَلَا تَحۡزَنُواْ
وَأَبۡشِرُواْ بِٱلۡجَنَّةِ ٱلَّتِي كُنتُمۡ تُوعَدُونَ ٣٠ نَحۡنُ أَوۡلِيَآؤُكُمۡ فِي ٱلۡحَيَوٰةِ ٱلدُّنۡيَا وَفِي ٱلۡأٓخِرَةِۖ
وَلَكُمۡ فِيهَا مَا تَشۡتَهِيٓ أَنفُسُكُمۡ وَلَكُمۡ فِيهَا مَا تَدَّعُونَ ٣١ نُزُلٗا مِّنۡ غَفُورٖ رَّحِيمٖ ٣٢

**30-32.** እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉና ከዚያ ቀጥ ያሉ አትፍሩ አትዘኑ። በዚያችም ተስፋ ቃል ትደረግላቸሁ። በነበራችሁት ገነት ተበሰሩ በማለት በእነርሱ ላይ መላዕክት ይወርዳሉ። እኛ በቅርቢቱም ሕይወት በመጨረሻይቱም ረዳቶቻችሁ ነን! ለእናንተም በእርሷ ውስጥ ነፍሶቻችሁ የሚሹት ሁሉ አላችሁ። ለእናንተም በእርሷ ውስጥ የምትፈልጉት ሁሉ አለላችሁ። መህሪ፤ አዛኝ ከሆነው አላህ መስተንግዶ ሲሆን ይባላሉ።

ከተብራራው ምዕራፍ (30) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የመካ ሙሽሪኮች ጌታችን አላህ መላኢኮች ሴት ልጆቹ አይሁዶች ደግሞ ጌታችን አላህ ዑዘይርን ልጁ በማለታቸው ሲጠሙ አቡበክር ግን ጌታዬ አላህ ሙሐመድ የአላህ መልዕክተኛና አገላጋዩ ናቸው በማለታቸው ትክክለኛ መሆናቸውን በግልፅ ለማስረዳት ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ)

وَمَنۡ أَحۡسَنُ قَوۡلٗا مِّمَّن دَعَآ إِلَى ٱللَّهِ وَعَمِلَ صَٰلِحٗا وَقَالَ إِنَّنِي مِنَ ٱلۡمُسۡلِمِينَ ٣٣

**33.** ወደ አላህ ከጠራንና መልካምን ከሰራ እኔ ከሙስሊሞች ነኝ ካለም ሰው ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን ነው?

وَلَا تَسۡتَوِي ٱلۡحَسَنَةُ وَلَا ٱلسَّيِّئَةُۚ ٱدۡفَعۡ بِٱلَّتِي هِيَ أَحۡسَنُ فَإِذَا ٱلَّذِي بَيۡنَكَ وَبَيۡنَهُۥ عَدَٰوَةٞ
كَأَنَّهُۥ وَلِيٌّ حَمِيمٞ ٣٤ وَمَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ٱلَّذِينَ صَبَرُواْ وَمَا يُلَقَّىٰهَآ إِلَّا ذُو حَظٍّ عَظِيمٖ ٣٥
وَإِمَّا يَنزَغَنَّكَ مِنَ ٱلشَّيۡطَٰنِ نَزۡغٞ فَٱسۡتَعِذۡ بِٱللَّهِۖ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ٣٦

**34-36.** መልካሚቱና ክፉይቱም ፀባይ አይስተካሉም በዚያች እርሷ መልካም በሆነችው ፀባይ መጥፎይቱን ገፍትር ያን ጊዜ በአንተና በእርሱ መካከል ጠብ ያለው ሰው እርሱ ልክ እንደ ወዳጅ ዘመድ ይሆናል። ይህችንም ፀባይ እነዚያን

የታገሱት እንጂ ሌላው አያገኛትም። የትልቅም እድል ባለቤት እንጂ ማንም አያገኛትም። ከሰይጣን ጉትጎታ ቢያገኝህ (ከመልካም ፀባይ ቢመልስህ) በአላህ ተጠበቅ እነሆ እርሱ ሰሚና አዋቂ ነውና።

وَمِنۡ ءَايَٰتِهِ ٱلَّيۡلُ وَٱلنَّهَارُ وَٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُۚ لَا تَسۡجُدُواْ لِلشَّمۡسِ وَلَا لِلۡقَمَرِ وَٱسۡجُدُواْ لِلَّهِ ٱلَّذِي خَلَقَهُنَّ إِن كُنتُمۡ إِيَّاهُ تَعۡبُدُونَ ۝٣٧ فَإِنِ ٱسۡتَكۡبَرُواْ فَٱلَّذِينَ عِندَ رَبِّكَ يُسَبِّحُونَ لَهُۥ بِٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَهُمۡ لَا يَسۡـَٔمُونَ ۩ ۝٣٨

**37-38.** ሌሊትና ቀንም ፀሀይና ጨረቃም ከምልክቶቹ ናቸው ለፀሐይና ለጨረቃ አትስገዱ ለዚያም ለፈጠራችሁ አላህ ስገዱ። እነርሱን ብቻ የምትገዙ እንደሆናችሁ ለሌላ አትስገዱ። ቢኮሩም እነዚያ በጌታህ ዘንድ ያሉት መላዕክት በቀንም በሌሊትም ለእርሱ ያወድሳሉ እነርሱም አይሰለቹም።

وَمِنۡ ءَايَٰتِهِۦٓ أَنَّكَ تَرَى ٱلۡأَرۡضَ خَٰشِعَةً فَإِذَآ أَنزَلۡنَا عَلَيۡهَا ٱلۡمَآءَ ٱهۡتَزَّتۡ وَرَبَتۡۚ إِنَّ ٱلَّذِيٓ أَحۡيَاهَا لَمُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰٓۚ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ۝٣٩

**39.** አናንተ ምድርን ደረቅ ሆና ማየትህም ከመልዕክቶቹ ነው። በእርሷም ላይ ውሃን ባወረድን ጊዜ በቡቃያዎችዋ ትላወሳለች፤ ተነፋለችም ያ ህያው ያደረጋት ጌታ በእርግጥ ሙታንን ህያው አድራጊ ነው። እርሱ በነገሩ ሁሉ ቻይ ነውና።

**ከተብራራው ምዕራፍ ከአንቀፅ (25-39) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ የሰው ልጆች ትክክለኛው መንገድ ለቆ መጥፎ ነገሮች ሲያዘወትር የሰይጣን ጓደኛ እንደሚልክበት፤
2. አጋሪዎች ኢስላምን የሚወጉበት የተንኮል መንገዶች ብዙ እንደነበሩ፤ የሙቶ መነሳት ሀቅነት ማረጋገጥ።
3. በህግ ላይ ቀጥ ማለት ያለው ምንዳ፤
4. ምእመናን የተሰጠው ብስራት፤
5. በጀነት ነፍስ የምትፈልገው ነገር ሁሉ እንዳለ፤
6. ወደ አላህ ጥሪ ማድረግ በአላህ ዘንድ ያለው ምንዳ፤
7. በኢስላም መኩራት ተገቢ አለመሆኑ፤
8. መጥፎ ነገርና መልካም ተግባር እኩል እንዳልሆኑ፤
9. ከሙስሊም ወንድሙ መጥፎ ነገር በመልካም ነገር መከላከል ግዴታ ስለመሆኑ፤
10. መጥፎ ነገር በደግ የሚመልስ ሰው ያለው ምንዳ፤
11. በአላህ ከሰይጣን መጠበቅ ግዴታ ስለመሆኑ፤
12. ተውሒድን ማረጋገጥ፤
13. ከሰዎች መካከል ለፀሀይ የሚያመልኩ እንዳሉ፤
14. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት በማስረጃ ማረጋገጥ፤
15. አላህ በሁሉ ነገር ቻይ እንደሆነ አንማራለን።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُلۡحِدُونَ فِيٓ ءَايَٰتِنَا لَا يَخۡفَوۡنَ عَلَيۡنَآۗ أَفَمَن يُلۡقَىٰ فِي ٱلنَّارِ خَيۡرٌ أَم مَّن يَأۡتِيٓ
ءَامِنٗا يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِۚ ٱعۡمَلُواْ مَا شِئۡتُمۡ إِنَّهُۥ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٌ ٤٠

**40.** እነዚያ አንቀፆቻችንን የሚያጣምሙ በእኛ ላይ አይደበቁም። የሚያጣምምና በእሳት ውስጥ የሚጣለው ሰው ይበልጣልን? ወይስ በትንሳኤ ቀን ፀጥተኛ ሆኖ የሚመጣው ሰው? ያሻችሁትን ስሩ ዋጋችሁን ታገናላችሁ። እርሱም የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

ከተብራራው ምዕራፍ (40) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በአቡጀህልና በመሰሎቹ ክህደትና በአቡበክርና በመሰሎቻቸው እምነት መካከል ያለውን ልዩነት ለመግለፅ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِٱلذِّكۡرِ لَمَّا جَآءَهُمۡۖ وَإِنَّهُۥ لَكِتَٰبٌ عَزِيزٞ ٤١ لَّا يَأۡتِيهِ ٱلۡبَٰطِلُ مِنۢ بَيۡنِ
يَدَيۡهِ وَلَا مِنۡ خَلۡفِهِۦۖ تَنزِيلٞ مِّنۡ حَكِيمٍ حَمِيدٖ ٤٢

**41-42.** እነዚያ በቁርኣን እርሱ አሸናፊ መጽሐፍ ሲሆን በመጣላቸው ጊዜ የካዱ ሁሉ ጠፊዎች ናቸው። ከኋላውም ከፊቱም ውሸት አይመጣበትም። ጥበበኛ ምስጉን ከሆነው ጌታ የተወረደ ነው።

مَّا يُقَالُ لَكَ إِلَّا مَا قَدۡ قِيلَ لِلرُّسُلِ مِن قَبۡلِكَۚ إِنَّ رَبَّكَ لَذُو مَغۡفِرَةٖ وَذُو عِقَابٍ أَلِيمٖ ٤٣

**43.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአንተ በፊት ለነበሩት መልዕክተኞች የተባለው ቢጤ እንጂ ለአንተ ሌላ አይባልም። ጌታህ የምህረት ባለቤትና የአሳማሚ ቅጣት ባለቤት ነው።

وَلَوۡ جَعَلۡنَٰهُ قُرۡءَانًا أَعۡجَمِيّٗا لَّقَالُواْ لَوۡلَا فُصِّلَتۡ ءَايَٰتُهُۥٓۖ ءَا۬عۡجَمِيّٞ وَعَرَبِيّٞۗ قُلۡ هُوَ لِلَّذِينَ
ءَامَنُواْ هُدٗى وَشِفَآءٞۚ وَٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ فِيٓ ءَاذَانِهِمۡ وَقۡرٞ وَهُوَ عَلَيۡهِمۡ عَمًىۚ أُوْلَٰٓئِكَ
يُنَادَوۡنَ مِن مَّكَانِۭ بَعِيدٖ ٤٤

**44.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአእጀምኛ የሆነ ቁርኣን ባረግነው ኖሮ አንቀፆች በምናውቀው ቋንቋ አይብራሩም ኖሯልን? ቁርኣኑ አእጅምኛና መልዕክተኛው አረባዊ ይሆናልን? ባሉ ነበር። እርሱ ለእነዚያ በአላህ ላመኑት ሰዎች መመሪያና መፈወሻ ነው። እነዚያም የማያምኑና በጆሮዎቻቸው ውስጥ ድንቁርና ነው (አይሰሙትም)። እርሱ በእነርሱ ላይ እውርነት ነው። እነዚያ ከሩቅ ስፍራ እንደሚጠሩ ናቸው።

ከተብራራው ምዕራፍ (44) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ቁረይሾች ይህ ቁርኣን በአረበኛና በአጀም ቋንቋ ለምን አልወረደም ነበር ብለው ስለጠየቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ሱዩጢ)

وَلَقَدْ ءَاتَيْنَا مُوسَى ٱلْكِتَٰبَ فَٱخْتُلِفَ فِيهِ ۗ وَلَوْلَا كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ لَقُضِىَ بَيْنَهُمْ ۚ وَإِنَّهُمْ لَفِى شَكٍّ مِّنْهُ مُرِيبٍ ﴿٤٥﴾

45. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳንም መጽሐፍንም በእርግጥ ሰጠነው በእርሱም ተለያየንበት ከጌታህም ያለፈች ቃል ባልነበረች ኖሮ በመካከላቸው በተፈረደ ነበር፤ እነርሱም በእርሱ አወላዋይ በሆነ ጥርጣሬ ውስጥ ናቸው፡፡

مَّنْ عَمِلَ صَٰلِحًا فَلِنَفْسِهِۦ ۖ وَمَنْ أَسَآءَ فَعَلَيْهَا ۗ وَمَا رَبُّكَ بِظَلَّٰمٍ لِّلْعَبِيدِ ﴿٤٦﴾

46. መልካም የሰራ ሰው ለነፍሱ ነው፡፡ ያጠፋም ሰው በእርሷ ላይ ነው፡፡ ጌታህም ለባሮቹ* በዳይ አይደለም፡፡

* ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «የሙስሊሞችና፤ የክርስቲያኖች የምሳሌ ልክ አንድ ሰው የተወሰኑ ስራ እስከ ለሊት ድረስ እንዲሰሩለት ሰዎችን በአንድ በተወሰነ ዋጋ እንደቀጠረ ነው፡፡ ሰዎቹም ስራውን እስከ እኩለ ቀን ድረስ ሰርተው «መጥፎም ነገር አልሰራንልህም ልትከፍለን የወሰንከውን ገንዘብህንም አንፈልግም» አሉት፡፡ እሱም «ይህን ዓይነቱን ድርጊትማ አትፈፅሙ፤ የቀረውን ስራ በሙሉ ሰርታችሁ ጨርሱና ደሞዛችሁን በአጠቃላይ ውሰዱ» አላቸው፡፡ እምቢ ብለው ትተውለት ሄዱ፡፡ ከነሱ በኋላ ሌሎች ሰራተኞች ቀጠረና «የቀረውን ጊዜያችሁን ስሩ የወሰንኩላችሁንም ገንዘብ ውሰዱ» አላቸው፡፡ ሰራተኞቹም እስከ ዐስር ድረስ ከሰሩ በኋላ «መጥፎ ነገር አንሰራንም የወስንከልንም ደሞዝ አንፈልግም» አሉት፡፡ እሱም «ከቀናችሁ የቀራችሁ ጥቂት ጊዜ ነውና ስራችሁን አጠናቁ» አላቸው፡፡ ሆኖም ግን እምቢኝ ብለው ትተውት ሄዱ፡፡ ሌሎች ሰዎችን እንዲሰሩለት ቀጠራቸው፡፡ እነዚህም የሁለቱን ስራዎች ፀሐይ እስከምትጠልቅ ድረስ ሰርተው አጠናቀቁና የሁለቱን ሰዎች ክፍያ ወሰዱ፡፡ ይህም እነዚያ የሙስሊሞች እና የሚመሩበትን ብርሃን በፍላጎት የወሰዱት ሰዎች ምሳሌ ነው»

۞ إِلَيْهِ يُرَدُّ عِلْمُ ٱلسَّاعَةِ ۚ وَمَا تَخْرُجُ مِن ثَمَرَٰتٍ مِّنْ أَكْمَامِهَا وَمَا تَحْمِلُ مِنْ أُنثَىٰ وَلَا تَضَعُ إِلَّا بِعِلْمِهِۦ ۚ وَيَوْمَ يُنَادِيهِمْ أَيْنَ شُرَكَآءِى قَالُوٓا۟ ءَاذَنَّٰكَ مَا مِنَّا مِن شَهِيدٍ ﴿٤٧﴾ وَضَلَّ عَنْهُم مَّا كَانُوا۟ يَدْعُونَ مِن قَبْلُ ۖ وَظَنُّوا۟ مَا لَهُم مِّن مَّحِيصٍ ﴿٤٨﴾

47-48. *የተንሳኤ መከሰቻ ሰዐቱን ማወቅ ወደ እርሱ ብቻ ይመለሳል፡፡ ከፍሬዎችም ከሽፋኖቻቸው አይወጡም ከሴትም አንዲትም አታረግዝም፤ አትወልድምም በእውቀት ቢሆን እንጂ፡፡ ተጋሪዎቸ የትኛቸው በማለት በሚጠራቸው ቀንም ከእኛ ውስጥ (ባለአንጣ አለ ብሎ) ምንም መስካሪ አለመኖሩን አስታወቅንህ ይላሉ፡፡ ያም በፊት ይገዙት የነበሩት ጣዖት ከእርሱ ይጠፉቸዋል፡፡ ለእርሱም ምንም መሸሻ የሌላቸው መሆኑን ያረጋግጣሉ፡፡

* ክፍል ሃያ አምስተኛ

لَّا يَسۡـَٔمُ ٱلۡإِنسَٰنُ مِن دُعَآءِ ٱلۡخَيۡرِ وَإِن مَّسَّهُ ٱلشَّرُّ فَيَـُٔوسٞ قَنُوطٞ ﴿٤٩﴾ وَلَئِنۡ أَذَقۡنَٰهُ رَحۡمَةٗ مِّنَّا
مِنۢ بَعۡدِ ضَرَّآءَ مَسَّتۡهُ لَيَقُولَنَّ هَٰذَا لِي وَمَآ أَظُنُّ ٱلسَّاعَةَ قَآئِمَةٗ وَلَئِن رُّجِعۡتُ إِلَىٰ رَبِّيٓ إِنَّ لِي
عِندَهُۥ لَلۡحُسۡنَىٰۚ فَلَنُنَبِّئَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِمَا عَمِلُواْ وَلَنُذِيقَنَّهُم مِّنۡ عَذَابٍ غَلِيظٖ ﴿٥٠﴾
وَإِذَآ أَنۡعَمۡنَا عَلَى ٱلۡإِنسَٰنِ أَعۡرَضَ وَنَـَٔا بِجَانِبِهِۦ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ فَذُو دُعَآءٍ عَرِيضٖ ﴿٥١﴾

**49-51.** ሰው በጎ ነገርን ከመለመን አይሰለችም። ክፉም ቢያገኘው ወዲያውኑ በጣም ተስፋ ቆራጭ ተበሳጭ ይሆናል። ካገኛቸውም መከራ በኋላ ከእኛ የሆነን እዝነት ብናቀምሰው ይህ ለእኔ በስራየ የተገባኝ ነው፤ ሰዓቲቱም መጪ ናት ብየ አላስብም ወደ ጌታየም ብመለስ ለእኔው እርሱ ዘንድ መልካሚቱ ገነት በእርግጥ አለችኝ ይላል። እነዚያንም የካዱትን ስራዎቻቸውን በእርግጥ እንነግራቸዋለን። ከበረታውም ስቃይም በእርግጥ እናቀምሳቸዋለን። በሰውም ላይ ፀጋችንን በለገስን ጊዜ ከማመስገን ይዞራል በጎኑም ይርቃል። መከራም ባገኘው ጊዜ የብዙ ልመና ባለቤት ይሆናል።

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِن كَانَ مِنۡ عِندِ ٱللَّهِ ثُمَّ كَفَرۡتُم بِهِۦ مَنۡ أَضَلُّ مِمَّنۡ هُوَ فِي شِقَاقِۭ بَعِيدٖ ﴿٥٢﴾

**52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በላቸው ንገሩኝ ቁርኣን ከአላህ ዘንድ ቢሆን ከዚያ በእርሱ ብትክዱም ከእውነት በራቀ ጭቅጭቅ ላይ ከሆነ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማን ነው።

سَنُرِيهِمۡ ءَايَٰتِنَا فِي ٱلۡأٓفَاقِ وَفِيٓ أَنفُسِهِمۡ حَتَّىٰ يَتَبَيَّنَ لَهُمۡ أَنَّهُ ٱلۡحَقُّۗ
أَوَلَمۡ يَكۡفِ بِرَبِّكَ أَنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ﴿٥٣﴾

**53.** እርሱም ቁርኣን እውነት መሆኑ ለእርሱ እስከሚገለፅላቸው ድረስ በአጽናፎቹ ውስጥና በነፍሶቻቸውም ውስጥ ያሉትን ታዕምራቶችን በእርግጥ እናሳያቸዋለን። ጌታህም እርሱ በነገሩ ሁሉ አዋቂ መሆኑ አይበቃቸውምን?

أَلَآ إِنَّهُمۡ فِي مِرۡيَةٖ مِّن لِّقَآءِ رَبِّهِمۡۗ أَلَآ إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَيۡءٖ مُّحِيطُۢ ﴿٥٤﴾

**54.** ሙስሊሞች ሆይ! አስተውሉ! እነርሱ ከጌታቸው መገኛኘት በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ሙስሊሞች ሆይ! አስተውሉ! እርሱ በነገሩ ሁሉ በእውቀቱ ከባቢ ነው።

**ከተብራራችው ምዕራፉ ከአንቀፅ (52-54) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩን (ﷺ) ማፅናናት፤
2. አጋሪዎች የነበራቸውን መጥፎ ባህሪና ክህደት ማጋለጥ፤
3. የቁርኣን መድሐኒትነት ለምእመናን እንጅ እንዳልሆነ፤
4. አላህ ላለፉት ህዝቦች የዋላቸው ውለታዎች፤
5. አላህ ከግፍ ተግባራት የፀዳ ስለ መሆኑ፤
6. ገይቦችን የሚያውቅ አላህ ብቻ ስለመሆኑ፤
7. አላህ ሁሉን ነገር እንደሚያውቅ፤
8. አጋሪዎች በትንሳኤ ዕለት ከማጋራት የፀዱ አለመሆናቸውን፤
9. የሰው ልጅ ወደ ኢስላም ከመግባቱ በፊት የነበረንና የሚኖረውን ባህሪ መግለፅ፤
10. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
11. ተስፋ መቁረጥና ኩራት ትዕቢትን ማውገዝ፤
12. በቁርኣን መካድን ማውገዝ፤
13. በቁርኣን ካስተባበለ ሰው የበለጠ ምንም ወንጀለኛ እንደሌለ፤
14. የአላህ ቃል ተፈፃሚነት፤
15. እስካሁንም የታዩትም ሆኑ ወደ ፊት የሚታዩ በዚህች አንቀፅ ውስጥ እንደሚጣቀለሉ፤
16. የኢስላም ሀቅነትና ትክክለኛነት ዓለም የሚያውቅበት ጊዜ ሩቅ እንዳልሆነ፤
17. የሙቶ መነሳት ሀቅነት ማረጋገጥን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የተብራራው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

ምዕራፍ (42)

# የምክክሩ ምዕራፍ

(ሱረቱ አሽ-ሹራ)

سُورَةُ الشُّورَىٰ

## በመካ የወረደ ምዕራፍ ነው። አናቅፅ (53) ናቸው።

## የሱረቱ አሽ-ሹራ መግቢያ

የምክክሩ ምዕራፍ ሐሚይም ዓይን ሲን ቃፍ ምዕራፍም ይባላል።

በመጀመሪያው ቁርአን ከአላህ የመጣ መሆኑንና እሱም ለተቃወሙት ካሀዲያን መልስ ሰጥቶ ነብዩን (ﷺ) በሰፊው ያፅናናል። ከዚያ ይህን ቁርአን ያወረደው አላህ ችሎታን ስፋትንና ግዝፈትን እንደ ካሀዲያን እውነቱን ግልፅ ሆኖላቸው ያስተማሩትን ህግ አንድነትና የከሓዲያንን አመፅ እንዲሁም ማጋራት ያወግዛል።

ሰዎች በዱንያ ላይ የሚያደርጉትን ወከባ አውግዞ ነብዩ (ﷺ) ቁርአንን ቀጥፈውት ነው የሚሉትን ካሀዲያን ያብጠለጥላል። ሌላ ቀርቶ ከቁርአን ውስጥ አንዷትን አጭር ምዕራፍ እንኳን የምታህል ማምጣት እንደማይችሉ እያወቁ አላህ ንሰሀ ገቢዎችን እንደሚቀበልና በሰዎችም ሀብታምና ደሃ የማድረጉን ምክንያት ይጠቁማል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

حمٓ ۝١ عٓسٓقٓ ۝٢

**1-2.** ሓ፣ ሚይም፣ ዓይን፣ ሲን፣ ቃፍ*

✷ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርአን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

كَذَٰلِكَ يُوحِيٓ إِلَيۡكَ وَإِلَى ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِكَ ٱللَّهُ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ۝٣
لَهُۥ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلۡعَلِيُّ ٱلۡعَظِيمُ ۝٤

**3-4.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልክ እንደዚሁ በዚህ ምእራፍ ውስጥ እንዳለው አሸናፊውና ጥበበኛው አላህ ወደ አንተ ያወርዳል። ወደ እነዚያም ከአንተ በፊት ወደ ነበሩት ህዝቦች አውርዷል። በሰማያትና በምድር ዉስጥ ያለው ሁሉ የእርሱ ብቻ ነው። እርሱም የሁሉም በላይ የሁሉም ታላቅ ነው።

تَكَادُ ٱلسَّمَٰوَٰتُ يَتَفَطَّرۡنَ مِن فَوۡقِهِنَّۚ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ يُسَبِّحُونَ بِحَمۡدِ رَبِّهِمۡ
وَيَسۡتَغۡفِرُونَ لِمَن فِي ٱلۡأَرۡضِۗ أَلَآ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ٥

5. ከበላያቸው ከሆነው ከአላህ ፍራቻ የተነሳ ሰማያት ሊቀደዱ ይቀርባሉ፤ መልአክትም ጌታቸውን እያመሰገኑ ያወሳሉ (ያጠራሉ)። በምድርም ላለው ፍጡር ሁሉ ምህረትን ይለምናሉ። ሙስሊሞች አስተዉሉ። አላህ መሀሪና አዛኝ ነው።

وَٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَ ٱللَّهُ حَفِيظٌ عَلَيۡهِمۡ وَمَآ أَنتَ عَلَيۡهِم بِوَكِيلٖ ٦
وَكَذَٰلِكَ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ قُرۡءَانًا عَرَبِيّٗا لِّتُنذِرَ أُمَّ ٱلۡقُرَىٰ وَمَنۡ حَوۡلَهَا وَتُنذِرَ يَوۡمَ ٱلۡجَمۡعِ
لَا رَيۡبَ فِيهِۚ فَرِيقٞ فِي ٱلۡجَنَّةِ وَفَرِيقٞ فِي ٱلسَّعِيرِ ٧

6-7. እነዚያም ከእርሱ ሌላ ጣዖታትን እረዳቶች አድርገው የያዙ ሁሉ አላህ በእነርሱ ላይ ተጠባባቂ ነው። አንተም በእነርሱ ላይ ሀላፊ አይደለህም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልክ እንደዚሁም የከተሞች እናት የሆነችውን የመካን ሰዎችና በአካባቢዋ ያሉትን ልታስፈራራ የመሰብሰቢያውንም ቀን በእርሱ ጥርጣሬ የሌለበት ሲሆን ልታስጠነቅቅ በአረበኛ ቋንቋ የሆነን ቁርአንን ወደ አንተ አወረድን። ከእርሱም ከፊሉ በገነት ውስጥ ከፊሉ ደግሞ በእሳት ውስጥ ነው።

وَلَوۡ شَآءَ ٱللَّهُ لَجَعَلَهُمۡ أُمَّةٗ وَٰحِدَةٗ وَلَٰكِن يُدۡخِلُ مَن يَشَآءُ فِي رَحۡمَتِهِۦۚ
وَٱلظَّٰلِمُونَ مَا لَهُم مِّن وَلِيّٖ وَلَا نَصِيرٍ ٨ أَمِ ٱتَّخَذُواْ مِن دُونِهِۦٓ أَوۡلِيَآءَۖ
فَٱللَّهُ هُوَ ٱلۡوَلِيُّ وَهُوَ يُحۡيِ ٱلۡمَوۡتَىٰ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٩

8-9. አላህ በፈለገ ኖሮ ሰዎችን በአንድ ሃይማኖት ላይ የሆኑ አንድ ህዝብ ባደረጋቸው ነበር። ግን የሚፈልገውን ሰው በእዝነቱ ውስጥ ያስገባዋል። በዳዮች ሁሉ ምንም ወዳጅና ረዳት የላቸውም። ከእርሱ ሌላ ረዳቶች ያዙን? (እነርሱ ረዳቶች አይደሉም) ትክክለኛ ረዳት አላህ ብቻ ነው። እርሱ ሙታንን ህያው ያደርጋል። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነውና።

وَمَا ٱخۡتَلَفۡتُمۡ فِيهِ مِن شَيۡءٖ فَحُكۡمُهُۥٓ إِلَى ٱللَّهِۚ ذَٰلِكُمُ ٱللَّهُ رَبِّي عَلَيۡهِ تَوَكَّلۡتُ وَإِلَيۡهِ
أُنِيبُ ١٠ فَاطِرُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ جَعَلَ لَكُم مِّنۡ أَنفُسِكُمۡ أَزۡوَٰجٗا وَمِنَ ٱلۡأَنۡعَٰمِ
أَزۡوَٰجٗا يَذۡرَؤُكُمۡ فِيهِۚ لَيۡسَ كَمِثۡلِهِۦ شَيۡءٞۖ وَهُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡبَصِيرُ ١١

**10-11.** (ሰዎች ሆይ)፣ ያ የተለያዩበት ነገር ሁሉ ፍርዱ ወደ አላህ ብቻ ነው። አላህ ጌታዬ ነው በእርሱ ላይ ተመካሁ። ወደ እርሱ ብቻ እመለሳለሁ በላቸው። ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው አላህ ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ከቤት እንስሳዎችም አይነቶችን (ወንዶችና ሴቶችን) ለእናንተ ፈጠረላችሁ። በዚህ ድርጊቱም ያባዛችኋል። የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱ ሁሉን ነገር ሰሚና ሁሉን ተመልካች ነው።

**ከምክክሩ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-10) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ተውሒድን ማስተማር የሁሉም ነብያት ጥሪ እንደነበር፤
2. የአላህን ትልቅነት መግለፅ፤
3. ነብዩን (ﷺ) ማፅናናት፤
4. የነብዩ (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
5. መካ የመንደሮች እናት ስለመሆንዋ፤
6. የሥራዎቻችን ምክንያት መጥቀስ፤
7. ሰዎች በትንሳኤ ዕለት እድለኞችና እድለቢሶች ሁነው እንደሚከፈሉ፤
8. አላህ ህዝቦች አንድ እንዳይሆኑ እራሱ ብቻ ምክንያቱን እንደሚያውቅ፤
9. ከአላህ ሌላ በሆነ ጥብቃ የፈለገ እንደሚከስር እንማራለን።

لَهُۥ مَقَالِيدُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ يَبۡسُطُ ٱلرِّزۡقَ لِمَن يَشَآءُ وَيَقۡدِرُۚ إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ ﴿١٢﴾

**12.** የሰማያትና የምድር ድልቦች መክፈቻዎች የእርሱ ብቻ ናቸው። ሲሳይን ለሚፈልገው ሰው ያሰፋል። ለሚፈልገዉም ያጠባል። እርሱ ሁሉን ነገር አዋቂ ነውና።

۞ شَرَعَ لَكُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا وَصَّىٰ بِهِۦ نُوحٗا وَٱلَّذِيٓ أَوۡحَيۡنَآ إِلَيۡكَ وَمَا وَصَّيۡنَا بِهِۦٓ إِبۡرَٰهِيمَ
وَمُوسَىٰ وَعِيسَىٰٓۖ أَنۡ أَقِيمُواْ ٱلدِّينَ وَلَا تَتَفَرَّقُواْ فِيهِۚ كَبُرَ عَلَى ٱلۡمُشۡرِكِينَ مَا تَدۡعُوهُمۡ إِلَيۡهِۚ
ٱللَّهُ يَجۡتَبِيٓ إِلَيۡهِ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِيٓ إِلَيۡهِ مَن يُنِيبُ ﴿١٣﴾

**13.** ሰዎች ሆይ፣ ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን ኑህን ያዘዝንበትን ያንንም ወደ አንተ ያወረድነውን ያንንም ኢብራሂምን፤ ሙሳንና ዒሳንም በሱ ያዘዝንበትን ሃይማኖትን በትክክል አቋቁሙ በእርሱም ላይ አትለያዩ በማለት ደነገገላችሁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ አጋሪዎች ያ ወደ እርሱ የምትጠራቸው ነገር ኢስላም ከበዳቸው። አላህ የሚፈልገውን ሰው ወደ እርሱ እምነት ይመርጣል። የሚመለስንም ሰው ወደ እርሱ ይመራል።

وَمَا تَفَرَّقُوٓا۟ إِلَّا مِنۢ بَعْدِ مَا جَآءَهُمُ ٱلْعِلْمُ بَغْيًۢا بَيْنَهُمْ ۚ وَلَوْلَا كَلِمَةٌ سَبَقَتْ مِن رَّبِّكَ إِلَىٰٓ أَجَلٍ
مُّسَمًّى لَّقُضِىَ بَيْنَهُمْ ۚ وَإِنَّ ٱلَّذِينَ أُورِثُوا۟ ٱلْكِتَٰبَ مِنۢ بَعْدِهِمْ لَفِى شَكٍّ مِّنْهُ مُرِيبٍ ١٤

**14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሃይማኖት ሰዎች እውቀት ከመጣላቸው በኋላ በመካከላቸው በምቀኝነት እንጂ በሌላ አልተለያዩም። እስከተወሰነ ጊዜ (በማቆየት) ከጌታህ ያለፈች ቃል ባልነበረች ኖሮ በእነርሱ መካከል አሁኑኑ በተፈረደ ነበር። እነዚያም ከኋላቸው መጽሐፍን እንዲወርሱ የተደረጉት ክፍሎች ከእርሱ በእርግጥ ባወላዋይ ጥርጣሬ ውስጥ ናቸው።

فَلِذَٰلِكَ فَٱدْعُ ۖ وَٱسْتَقِمْ كَمَآ أُمِرْتَ ۖ وَلَا تَتَّبِعْ أَهْوَآءَهُمْ ۖ وَقُلْ ءَامَنتُ بِمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِن
كِتَٰبٍ ۖ وَأُمِرْتُ لِأَعْدِلَ بَيْنَكُمُ ۖ ٱللَّهُ رَبُّنَا وَرَبُّكُمْ ۖ لَنَآ أَعْمَٰلُنَا وَلَكُمْ أَعْمَٰلُكُمْ ۖ لَا حُجَّةَ
بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمُ ۖ ٱللَّهُ يَجْمَعُ بَيْنَنَا ۖ وَإِلَيْهِ ٱلْمَصِيرُ ١٥

**15.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እዚህ መንገድም (ኃይንንና ሰዎችን) ጥራ። እንደታዘዝከውም ቀጥ በል ዝንባሌያቸውን አትከተል። ከመጽሐፍ አላህ ባወረደው ሁሉ አመንኩ። በመካከላችሁ በፍርድ ላስተካክልም ታዘዝኩ። አላህ ጌታችን ጌታችሁም ነው። ለእኛ ስራዎቻችን አሉን። ለእናንተም እንዲሁ ስራዎቻችሁ አሏችሁ። በእኛና በእናንተ መካከል ክርክር የለም። አላህ በመካከላችን ይሰበስባል። መመለሻው ወደ እርሱ ብቻ ነው በላቸው።

وَٱلَّذِينَ يُحَآجُّونَ فِى ٱللَّهِ مِنۢ بَعْدِ مَا ٱسْتُجِيبَ لَهُۥ حُجَّتُهُمْ دَاحِضَةٌ عِندَ رَبِّهِمْ وَعَلَيْهِمْ
غَضَبٌ وَلَهُمْ عَذَابٌ شَدِيدٌ ١٦ ٱللَّهُ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ ٱلْكِتَٰبَ بِٱلْحَقِّ وَٱلْمِيزَانَ ۗ وَمَا يُدْرِيكَ لَعَلَّ
ٱلسَّاعَةَ قَرِيبٌ ١٧ يَسْتَعْجِلُ بِهَا ٱلَّذِينَ لَا يُؤْمِنُونَ بِهَا ۖ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مُشْفِقُونَ مِنْهَا
وَيَعْلَمُونَ أَنَّهَا ٱلْحَقُّ ۗ أَلَآ إِنَّ ٱلَّذِينَ يُمَارُونَ فِى ٱلسَّاعَةِ لَفِى ضَلَٰلٍۭ بَعِيدٍ ١٨

**16-18.** እነዚያ በአላህ ሃይማኖት ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የሚከራከሩት ሰዎች ማስረጃዎቻቸው በጌታቸው ዘንድ ብልሹ (ዉድቅ) ናቸው። በእነርሱም ላይ የአላህ ቁጣ አለባቸው (ወደቀባቸው)። ለእነርሱም ብርቱ ቅጣት አለላቸው። አላህ ያ መጽሐፉን በእርግጥ ያወረደ ነው። ሚዛንንም እንደዚሁ ያወረደ ነው። ሰዓቲቱን ምን አልባትም ቅርብ ብትሆን ምን አሳወቀህ?። እነዚያ በእርሷ የማያምኑት በእርሷ ያቻኩላሉ። እነዚያም በአላህ ያመኑት ከእርሷ ፈሪዎች ናቸው። እርሷም እውነት መሆኗን በትክክል ያውቃሉ። (ሙስሊሞች)

አስተውሉ። እነዚያ በሰዓቲቱ የሚከራከሩ ሰዎች ሁሉ በእርግጥ ከእውነት በራቀ ስህተት ውስጥ ናቸው።

ከምክክሩ ምዕራፍ (16) ኛ አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- መፅሐፋችን ከመፅሐፋችሁ በፊት የወረደ ነብያችን ከነብያችሁ በፊት የተላከ በመሆኑ እምነታችን ከእምነታችሁ ይበልጣል። በማለት ሰዎችን ከኢስላም ለማደናቀፍ ያስወሩ በነበሩ አይሁዶች ነው የወረደው። (ሱዩጢ)

ٱللَّهُ لَطِيفُۢ بِعِبَادِهِۦ يَرۡزُقُ مَن يَشَآءُۖ وَهُوَ ٱلۡقَوِيُّ ٱلۡعَزِيزُ ١٩

**19.** አላህ ለባሮቹ በጣም ሩህሩህ ነው። ለሚፈልገው ሰው ሁሉ በሰፊው ሲሳይን ይሰጣል። እርሱም ብርቱ እና አሸናፊ ነው።

مَن كَانَ يُرِيدُ حَرۡثَ ٱلۡأٓخِرَةِ نَزِدۡ لَهُۥ فِي حَرۡثِهِۦۖ وَمَن كَانَ يُرِيدُ حَرۡثَ ٱلدُّنۡيَا نُؤۡتِهِۦ مِنۡهَا وَمَا لَهُۥ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ مِن نَّصِيبٍ ٢٠ أَمۡ لَهُمۡ شُرَكَٰٓؤُاْ شَرَعُواْ لَهُم مِّنَ ٱلدِّينِ مَا لَمۡ يَأۡذَنۢ بِهِ ٱللَّهُۚ وَلَوۡلَا كَلِمَةُ ٱلۡفَصۡلِ لَقُضِيَ بَيۡنَهُمۡۗ وَإِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ لَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ ٢١

**20-21.** በስራው የኋለኛይቱን ዓለም አዝመራ የሚፈልግ ሰው ለእርሱ በአዝመራው ላይ ሌላን እንጨምርለታለን። የቅርቢቱን ዓለም አዝመራ የሚፈልግ ሰው ግን በእርሷ የተወሰነለትን ብቻ እንሰጠዋለን። ለእርሱም በኋለኛይቱ ዓለም ምንም ድርሻ የለውም። (ከሓዲያን) ከአላህ ያልተፈቀደውን ሃይማኖት የደነገጉ ተጋሪዎች አሏቸውን? የፍርዱ ቃል ባልነበረ ኖሮ በመካከላቸው አሁኑኑ በተፈረደ ነበር። በደለኞችም ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት በእርግጥ አለላቸው።

**ከምክክሩ ምዕራፍ ከአንቀፅ (17-21) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የተለያዩበትን ነገር ወደ አላህ መመለስ ተገቢ ስለመሆኑ፤
2. በአላህ ላይ መመካት ተገቢ ስለመሆኑ፤
3. አላህን በፍጡር ከመመሰል ማጥራት ተገቢ ስለመሆኑ፤
4. አላህ ፍጡሩን መጋቢ መሆኑንና የሰዎች ርዝቅ በእሱ እጅ ብቻ መሆኑ፤
5. በአላህ ዲን ላይ መለያየት ክልክል ስለመሆኑ፤
6. በዲን ላይ ያሉ ልዩነቶች መነሻው ምቀኝነትና፤
7. ወደ ኢስላም ጥሪ ማድረግ የሁሉም ግዴታ ስለመሆኑ፤
8. ስሜቶችን መከተል ክልክል ስለመሆኑ፤
9. በኢስላም ላይ ቀጥ ብሎ መቀጠል ግዴታ ስለመሆኑ፤
10. የአላህ ዲን አንድ ስለመሆኑ፤
11. በአላህ ዲን ላይ መለያየት ክልክል ስለመሆኑ፤
12. ከመፅሐፍ ሰዎች ጋር ክርክር ከማድረግ መቆጠብ እንዳለኢብኑ፤
13. ቁርኣን የወረደበት ጥበብና ምክንያት፤

14. የትንሳኤ ቀን ቅርብ መሆን፤
15. ትንሳኤን ለምን አይደርስም እያሉ መጠየቅ የከሓዲያን ተግባር መሆኑ፤
16. አላህ ለባሮቹ አዛኝ ስለመሆኑ፤
17. ኒያን ማሳመር ግዳጅ ስለመሆኑ፤
18. ከአላህና ከነብዩ (ﷺ) በስተቀር ህግ መዳን ግን የማንም ስልጣን እንዳልሆነ እንማራለን።

تَرَى ٱلظَّٰلِمِينَ مُشْفِقِينَ مِمَّا كَسَبُواْ وَهُوَ وَاقِعُۢ بِهِمْۗ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ
فِي رَوْضَاتِ ٱلْجَنَّاتِۖ لَهُم مَّا يَشَآءُونَ عِندَ رَبِّهِمْۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلْفَضْلُ ٱلْكَبِيرُ ﴿٢٢﴾ ذَٰلِكَ ٱلَّذِي
يُبَشِّرُ ٱللَّهُ عِبَادَهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِۗ قُل لَّآ أَسْـَٔلُكُمْ عَلَيْهِ أَجْرًا إِلَّا ٱلْمَوَدَّةَ
فِي ٱلْقُرْبَىٰۗ وَمَن يَقْتَرِفْ حَسَنَةً نَّزِدْ لَهُۥ فِيهَا حُسْنًاۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ شَكُورٌ ﴿٢٣﴾

**22-23.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በደለኞችን በሰሩት ስራ ዋጋ በትንሳኤ ቀን ፈሪዎች ሆነው ታያቸዋለህ። እርሱም በእነርሱ ላይ የማይቀር ወዳቂ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ ያመኑና መልካም ስራን የሰሩ ሁሉ በገነት ጨፌዎች ዉስጥ ናቸው። ለእነርሱም በጌታቸው ዘንድ የሚፈልጉት ሁሉ አለላቸው። ይህ እርሱ ታላቅ ችሮታ ነው። ያ አላህ እነዚያ በትክክል ያመኑትንና መልካሞችን የሰሩት ባሮቹን የሚያበስርበት ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በእርሱ መልዕክቴን በማድረሴ ላይ የዝምድና ውዴታን እንጂ ሌላ ዋጋ አልጠይቃችሁም በላቸው። መልካም ስራ የሚሰራ ሰው ሁሉ ለእርሱ በእርሷ ላይ መልካም ነገርን እንጨምርለታለን። አላህ መሀሪ እና አመስጋኝ ነውና።

ከምክክሩ ምዕራፍ (23) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) መዲና በገቡበት ጊዜ የተለያዩ ችግሮች ያጋጥሟቸው ነበረና እጃቸው ላይ ምንም ስላነበር አንሷሮች ወደ አላህ መርቷችሁ ልታይህ እጆችህ ልጅ ነው ችግር አለበትና ትንሽ ትንሽ እንኳን ብትሰበስቡለት ጥሩ ነው ተባብለው ገንዘብ አሰባስበው አምጥተው ለነበዩ (ﷺ) ሲነግሯቸው እነኚህ አናቅፅ ወረዱ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَمْ يَقُولُونَ ٱفْتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبًاۖ فَإِن يَشَإِ ٱللَّهُ يَخْتِمْ عَلَىٰ قَلْبِكَۗ وَيَمْحُ ٱللَّهُ ٱلْبَٰطِلَ وَيُحِقُّ
ٱلْحَقَّ بِكَلِمَٰتِهِۦٓۚ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿٢٤﴾

**24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአላህ ላይ ውሸትን ቀጠፈ ይላሉን? አላህም ቢፈልግ በልብህ ላይ ያትማል። አላህ ውሸትን ያብሳል። እውነትንም በቃላት ያረጋግጣል። እርሱ በይፋ የተነገሩት ቀርቶ በልቦች ውስጥ ያለውን ሁሉ አዋቂ ነውና።

وَهُوَ ٱلَّذِى يَقْبَلُ ٱلتَّوْبَةَ عَنْ عِبَادِهِۦ وَيَعْفُوا۟ عَنِ ٱلسَّيِّـَٔاتِ وَيَعْلَمُ مَا تَفْعَلُونَ ﴿٢٥﴾
وَيَسْتَجِيبُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ وَيَزِيدُهُم مِّن فَضْلِهِۦ ۚ وَٱلْكَـٰفِرُونَ لَهُمْ
عَذَابٌ شَدِيدٌ ﴿٢٦﴾ ۞ وَلَوْ بَسَطَ ٱللَّهُ ٱلرِّزْقَ لِعِبَادِهِۦ لَبَغَوْا۟ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَـٰكِن يُنَزِّلُ بِقَدَرٍ
مَّا يَشَآءُ ۚ إِنَّهُۥ بِعِبَادِهِۦ خَبِيرٌۢ بَصِيرٌ ﴿٢٧﴾

**25-27.** እርሱ (አላህ) ያ ሁልጊዜም ከባሮቹ ንስሀን የሚቀበል ኃጢአቶችንም ይቅር የሚል* የምትሰሩትን ሁሉ የሚያውቅ ጌታ ነው። እነዚያ በአላህ ያመኑትና መልካም ተግባሮችን የሰሩትን ልመናቸውን ይቀበላል። ከችሮታውም ይጨምርላቸዋል። ከሓዲያንም ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አለላቸው። አላህም ለባሮቹ ሁሉ ሲሳይን በዘረጋ ኖሮ በምድር ውስጥ ሁሉም ወሰን ባለፉ ነበር ግን የሚፈልገውን በልክ ያወርዳል። እርሱ በባሮቹ ውስጠ ዐዋቂ፤ ተመልካች ነውና።

* የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «ከአላህ በኩል የሆነን የይቅርታ ማግኛ መንገድ «አልላሁምም አንተ ረብቢ ለኢለሀ ኢልላ አንተ፤ አንተ ኸልቅተኒ ወአና ዐብዱከ ወአና ዐላ ዐህዲከ ወመዕዲከ መስተጣዕቱ አዑዙ ቢከ ሚንሸርሪ ማ ሰነዕቱ አቡኡ ለከ ቢኒዕመቲከ ዐለይየ ወአቡኡ ቢዘንቢ ፈግፊር ሊ ፈኢንነሁ ላ የግፊሩ አዝ. ዘነብ ኢልላ አንተ» የሚለው ነው አንድ ሰው በቀን ውስጥ ይህን በፅኑ እምነት ካለና በዚሁ ቀን ፀሐይ ከመጥለቋ በፊት ከሞተ ከጀነት ሰዎች መካከል ይሆናል። እንዲሁም አንድ ሰው ምሽት ላይ ይህን በፅኑ እምነት ካለና ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ከሞተ ከጀነት ሰዎች መካከል ይሆናል።

የዚህ ዱዓእ ትርጉም «ጌታዬ ሆይ! አንተ ጌታዬ ነህ፤ ካንተ በስተቀር አምልኮ የሚገባው አምላክ የለም፤ አንተ ፈጥረኸኛል እኔም ባሪያ ነኝ። እኔም የቻልኩትን ያህል ላንተ ባለኝ እምነትና ቃል ኪዳን ላይ የፀናሁ ነኝ። ከሰራሁት ኃጢአት ባንተ እጠበቃለሁ። አንተ በእኔ ላይ የዋልከውን ውለታ እያወኩኝ ወዳንተ ቀርቤያለሁ። እንዲሁም ኃጢአቴንም ወዳንተ አቅርቤያለሁ። ጌታዬ ሆይ! ማረኝም እንነሆ ካንተ በስተቀር ኃጢአትን የሚምር የለም።»

وَهُوَ ٱلَّذِى يُنَزِّلُ ٱلْغَيْثَ مِنۢ بَعْدِ مَا قَنَطُوا۟ وَيَنشُرُ رَحْمَتَهُۥ ۚ وَهُوَ ٱلْوَلِىُّ ٱلْحَمِيدُ ﴿٢٨﴾

**28.** እርሱ አላህ ያ ተስፋ ከቆረጡ በኋላ ዝናብን የሚያወርድ ችሮታውን የሚዘረጋ ነው። እርሱም ረዳትና ምስጉን ነውና።

ከምክክሩ ምዕራፍ (28) ኛ አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡- ሰዎች መጥተው ለዑመር ችግሩ በረታ፤ ሰው ተስፋ ቆረጠ ሲሏቸው አሁን እንግዲህ ዝናብ መዝነቡ ነው አሉና ይህን አንቀፅ አነበቡ። ይህ ማለት ችግሮች በበረቱ ቁጥር መፍትሔዎችን ያስከትላል ማለትን እንረዳለን ማለታቸው ነው።

وَمِنْ ءَايَـٰتِهِۦ خَلْقُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ وَمَا بَثَّ فِيهِمَا مِن دَآبَّةٍ ۚ
وَهُوَ عَلَىٰ جَمْعِهِمْ إِذَا يَشَآءُ قَدِيرٌ ﴿٢٩﴾

**29.** ሰማያትንና ምድርን መፍጠሩ ከተንቀሳቃሽም በሁለቱ ውስጥ የበተነው መፈጠሩ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ከፊሎቹ ናቸው። እርሱም በሚፈልግ ጊዜ እነርሱን በመሰብሰብ ቻይ ነው።

وَمَآ أَصَٰبَكُم مِّن مُّصِيبَةٖ فَبِمَا كَسَبَتۡ أَيۡدِيكُمۡ وَيَعۡفُواْ عَن كَثِيرٖ ﴿٣٠﴾

**30.** (ሰዎች ሆይ!) ማንኛውም መከራ ያገኛችሁ እጆቻችሁ በሰሩት ኃጢአት ምክንያት ብቻ ነው። ብዙውንም ይቅር ይላል።

وَمَآ أَنتُم بِمُعۡجِزِينَ فِي ٱلۡأَرۡضِۖ وَمَا لَكُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ مِن وَلِيّٖ وَلَا نَصِيرٖ ﴿٣١﴾

**31.** (ሰዎች ሆይ!) እናንተ በምድር ውስጥ አሸናፊዎች (አምላጮች) አይደላችሁም። ለእናንተም ከአላህ ሌላ ወዳጅም ሆነ ረዳት ምንም የላችሁም።

**ከምክክሩ ምዕራፍ ከአንቀፅ (21-31) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የዝምድና መብት ማረጋገጥ፤
2. ነብዩ (ﷺ) በአላህ እንደማይዋሹ፤
3. መልካምን ስራ ምንዳው እጥፍ ድርብ ስለመሆኑ፤
4. ተውባህ ግዴታ ስለመሆኑ ሸርጡ ከተሟላ አላህም እንደሚቀበለው፤
5. የመልካም ስራ ባለቤቶችን ሰዎች ዱዓ አላህ እንደሚቀበለው፤
6. የሰዎችን ሲሳይ የማበላለጡ ምክንያት፤
7. የአላህ ኃያልነት መግለጫ ክንውኖች፤
8. ሕግን መንቀፍ ችግር እንደሚያስከትል፤
9. በንብረትም ሆነ በህይወት የሚደርስ ችግር በራሱ ስህተት መሆኑን፤
10. ከወንጀሎች መካከል ሊማሩ የሚቻሉ ነገሮች እንዳሉ እንማራለን።

وَمِنۡ ءَايَٰتِهِ ٱلۡجَوَارِ فِي ٱلۡبَحۡرِ كَٱلۡأَعۡلَٰمِ ﴿٣٢﴾ إِن يَشَأۡ يُسۡكِنِ ٱلرِّيحَ فَيَظۡلَلۡنَ رَوَاكِدَ عَلَىٰ
ظَهۡرِهِۦٓۚ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَأٓيَٰتٖ لِّكُلِّ صَبَّارٖ شَكُورٍ ﴿٣٣﴾

**32-33.** በባህር ላይ እንደ ጋራዎች ሆነው ተንሻላዩቹም (መርከቦች) ከአስደናቂ ምልክቶቹ ናቸው። ቢፈልግ ንፋሱን የረጋ ያደርገዋል። ከዚያ መርከቦች በባህሩ ጀርባ ላይ የረጉ ይሆናሉ። በዚህ ውስጥ በጣም ታጋሽ፤ አመስጋኝ ለሆኑ ሰዎች ሁሉ በእርግጥም ብዙ ምልክቶች (ተዓምራት) አሉ።

أَوۡ يُوبِقۡهُنَّ بِمَا كَسَبُواْ وَيَعۡفُ عَن كَثِيرٖ ﴿٣٤﴾
وَيَعۡلَمَ ٱلَّذِينَ يُجَٰدِلُونَ فِيٓ ءَايَٰتِنَا مَا لَهُم مِّن مَّحِيصٖ ﴿٣٥﴾

**34-35.** ወይም ተሳፋሪዎች በሰሩት ኃጢአት ምክንያት እነርሱን በባህሩ በማስመጥ ያጠፉቸዋል፡፡ ከብዙም ጥፋቶች ይቅርታ ያደርጋል፡፡ ከእነርሱ መካከል እነዚያን በአንቀፆቻችን የሚከራከሩትን ሰዎች ለማወቅ ያጠፉቸዋል፡፡ ለእነርሱም ከእሱ ሌላ ምንም መሸሻ የላቸውም፡፡

فَمَآ أُوتِيتُم مِّن شَيْءٍ فَمَتَٰعُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَا ۖ وَمَا عِندَ ٱللَّهِ خَيْرٌ وَأَبْقَىٰ لِلَّذِينَ ءَامَنُوا۟
وَعَلَىٰ رَبِّهِمْ يَتَوَكَّلُونَ ﴿٣٦﴾ وَٱلَّذِينَ يَجْتَنِبُونَ كَبَٰٓئِرَ ٱلْإِثْمِ وَٱلْفَوَٰحِشَ وَإِذَا مَا غَضِبُوا۟ هُمْ
يَغْفِرُونَ ﴿٣٧﴾ وَٱلَّذِينَ ٱسْتَجَابُوا۟ لِرَبِّهِمْ وَأَقَامُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَأَمْرُهُمْ شُورَىٰ بَيْنَهُمْ وَمِمَّا
رَزَقْنَٰهُمْ يُنفِقُونَ ﴿٣٨﴾ وَٱلَّذِينَ إِذَآ أَصَابَهُمُ ٱلْبَغْيُ هُمْ يَنتَصِرُونَ ﴿٣٩﴾ وَجَزَٰٓؤُا۟ سَيِّئَةٍ سَيِّئَةٌ
مِّثْلُهَا ۖ فَمَنْ عَفَا وَأَصْلَحَ فَأَجْرُهُۥ عَلَى ٱللَّهِ ۚ إِنَّهُۥ لَا يُحِبُّ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٤٠﴾

**36-40.** (ሰዎች ሆይ)፣ የተሰጣችሁት ነገር ሁሉ የቅርቢቱ ሕይወት መጠቃቀሚያ ብቻ ነው፡፡ በአላህ ዘንድ ያለው ምንዳ ግን ለእነዚያ በትክክል በእሱ ለአመኑትና በጌታቸው ላይ ብቻ ለሚመኩት ሁሉ በላጭና ሁልጊዜ ነዋሪ ነው፡፡ ለእነዚያ ታላላቅ ሃጢያቶችንና ዝሙትን የሚርቁ፤ በተቆጡም ጊዜ የሚይምሩ ለሆኑት፤ ለእነዚያ የጌታቸውን ጥሪ አሚን ብለው ለተቀበሉት፤ ሶላትን ለአዘወተሩት፤ በሁሉ ነገራቸው ላይ በመካከላቸው መመካከር ልምዳቸው ለሆነው፤ ከሰጠናቸውም ሲሳይ ለሚለግሱት፤ ለእነዚያም በደል በደረሰባቸው ጊዜ በመሰሉ የሚመልሱ ለሆኑት (ከአላህ ዘንድ ያለው በላጭና ነዋሪ ነው)፡፡ የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ዋጋው ተመሳሳዩ መጥፎ ነው፡፡ ይቅር ያለና ያሳመረ ሰው ደግሞ ምንዳው በአላህ ላይ ብቻ ነው፡፡ እርሱ በደለኞችን አይወድምና፡፡

وَلَمَنِ ٱنتَصَرَ بَعْدَ ظُلْمِهِۦ فَأُو۟لَٰٓئِكَ مَا عَلَيْهِم مِّن سَبِيلٍ ﴿٤١﴾ إِنَّمَا ٱلسَّبِيلُ عَلَى ٱلَّذِينَ
يَظْلِمُونَ ٱلنَّاسَ وَيَبْغُونَ فِى ٱلْأَرْضِ بِغَيْرِ ٱلْحَقِّ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿٤٢﴾

**41-42.** እነዚያ ከተበደሉ በኋላ በመሰሉ የተበቀሉ በእነርሱ ላይ ምንም የወቀሳ መንገድ የለባቸውም፡፡ የወቀሳ መንገዱ በእነዚያ ሰዎችን በሚበድሉት እና በምድር ውስጥ ያለ ህግ ወሰንን በሚያልፉት ሰዎች ላይ ብቻ ነው፡፡ እነዚያ ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለላቸው፡፡

وَلَمَن صَبَرَ وَغَفَرَ إِنَّ ذَٰلِكَ لَمِنْ عَزْمِ ٱلْأُمُورِ ﴿٤٣﴾

**43.** የታገሰና ምህረት ያደረገ ሰው ይህ ተግባር ከተፈላጊ ነገሮች አንዱ ነው፡፡

وَمَن يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِن وَلِيّٖ مِّنۢ بَعۡدِهِۦۗ وَتَرَى ٱلظَّٰلِمِينَ لَمَّا رَأَوُاْ ٱلۡعَذَابَ يَقُولُونَ
هَلۡ إِلَىٰ مَرَدّٖ مِّن سَبِيلٖ ﴿٤٤﴾ وَتَرَىٰهُمۡ يُعۡرَضُونَ عَلَيۡهَا خَٰشِعِينَ مِنَ ٱلذُّلِّ يَنظُرُونَ مِن
طَرۡفٍ خَفِيّٖۗ وَقَالَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّ ٱلۡخَٰسِرِينَ ٱلَّذِينَ خَسِرُوٓاْ أَنفُسَهُمۡ وَأَهۡلِيهِمۡ يَوۡمَ
ٱلۡقِيَٰمَةِۗ أَلَآ إِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ فِي عَذَابٖ مُّقِيمٖ ﴿٤٥﴾ وَمَا كَانَ لَهُم مِّنۡ أَوۡلِيَآءَ يَنصُرُونَهُم مِّن
دُونِ ٱللَّهِۗ وَمَن يُضۡلِلِ ٱللَّهُ فَمَا لَهُۥ مِن سَبِيلٍ ﴿٤٦﴾

**44-46.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የሚያጠመውን ሰው ከእርሱ ማጥመም በኋላ ለእርሱ ምንም ወዳጅ የለውም። በደለኞች ቅጣትን ባዩ ጊዜ ለመመለስ መንገድ አለን? የሚሉ ሲሆኑ ታያቸዋለህ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከውርደት* የተነሳ ፈሪዎች ሆነው በዓይን ስርቆት ወደ እሳት እያስተዋሉ በእርሷ ላይ የሚቀርቡ ሁነው ታያቸዋለህ። እነዚያ በአላህ ያመኑት፡- በእርግጥ ከሳሪዎች ማለት እነዚያ ነፍሶቻቸውንና ቤተሰቦቻቸውን በትንሳኤ ቀን ያከሰሩት ናቸው ይላሉ። (ሙስሊሞች) አስተዉሉ። በደለኞች በእርግጥ ዘወታሪ ስቃይ ውስጥ ናቸው። ለእነርሱም ከአላህ ሌላ የሚረዷቸው ዘመዶች ምንም አልነበሯቸውም። አላህ የሚያጠመው ሰው ሁሉ ለእርሱ ወደ እውነት የሚመለስበት ምንም መንገድ የለውም።

* ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አንድ ሰው መጣና የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ከሓዲያንን በትንሳኤ ቀን በፊታቸው የተደፉ ሆነው ይነሳሉን? ብሎ ጠየቃቸው። እሳቸውም «በምድር ላይ ከሁለት እግሮቹ እንዲሄድ ያደረገው በትንሳኤ ቀን በፊቱ ተደፍቶ እንደሄድ ለማድረግ ይሳነዋልን?» አሉት። ቀታደህም «እንዴታ በጌታችን ክብር አይሳነውም» አሉ።

ٱسۡتَجِيبُواْ لِرَبِّكُم مِّن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَ يَوۡمٞ لَّا مَرَدَّ لَهُۥ مِنَ ٱللَّهِۚ
مَا لَكُم مِّن مَّلۡجَإٖ يَوۡمَئِذٖ وَمَا لَكُم مِّن نَّكِيرٖ ﴿٤٧﴾

**47.** (ከሓዲያን ሆይ)፣ ያ ከአላህ ከመጣ መላሽ የሌለለው ቀን ከመምጣቱ በፊት ለጌታችሁ ታዘዙ። በዚያ ቀን ለእናንተ ምንም መጠጊያም ሆነ መመኪያ (መደበቂያ ወይም ረዳት) የላችሁም።

فَإِنۡ أَعۡرَضُواْ فَمَآ أَرۡسَلۡنَٰكَ عَلَيۡهِمۡ حَفِيظًاۖ إِنۡ عَلَيۡكَ إِلَّا ٱلۡبَلَٰغُۗ وَإِنَّآ إِذَآ أَذَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ
مِنَّا رَحۡمَةٗ فَرِحَ بِهَاۖ وَإِن تُصِبۡهُمۡ سَيِّئَةُۢ بِمَا قَدَّمَتۡ أَيۡدِيهِمۡ فَإِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ كَفُورٞ ﴿٤٨﴾

**48.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቢዞሩም ወቀሳ የለብህም። በእነርሱ ላይ ጠባቂ አድረገን አላክንህምና። በአንተ ላይ ማድረስ እንጂ ሌላ የለብህም። እኛም ሰውን ከእኛ የሆነን ፀጋ ባቀመስነው ጊዜ በእርሷ ይደሰታል። እጆቻቸው ባስቀደሙት ኃጢአት ምክንያት መከራ ብትደርስባቸው ደግሞ ተስፋ ይቆርጣሉ። ሰው ለውለታ በጣም ከሓዲ ነውና።

لِّلَّهِ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ يَخْلُقُ مَا يَشَآءُ ۚ يَهَبُ لِمَن يَشَآءُ إِنَٰثًا وَيَهَبُ لِمَن يَشَآءُ ٱلذُّكُورَ ﴿٤٩﴾ أَوْ يُزَوِّجُهُمْ ذُكْرَانًا وَإِنَٰثًا ۖ وَيَجْعَلُ مَن يَشَآءُ عَقِيمًا ۚ إِنَّهُۥ عَلِيمٌ قَدِيرٌ ﴿٥٠﴾

**49-50.** የሰማያትና የምድር ንግስና የአላህ ብቻ ነው። የሚፈልገውን ይፈጥራል። ለሚፈልገው ሰው ሴቶችን ልጆች ይሰጣል። ለለሚፈልገውም ሰው ወንዶችን ይሰጣል። ወይም ወንዶችንና ሴቶችን አድርጎ ያጠናዳቸዋል። የሚፈልገውንም ሰው መካን ያደርገዋል። እርሱ ሁሉን አዋቂና ሁሉን ቻይ ነውና።

۞ وَمَا كَانَ لِبَشَرٍ أَن يُكَلِّمَهُ ٱللَّهُ إِلَّا وَحْيًا أَوْ مِن وَرَآئِ حِجَابٍ أَوْ يُرْسِلَ رَسُولًا فَيُوحِىَ بِإِذْنِهِۦ مَا يَشَآءُ ۚ إِنَّهُۥ عَلِىٌّ حَكِيمٌ ﴿٥١﴾

**51.** ሰው አላህ በራዕይ፤ ወይም ከግርዶ ወዲያ፤ ወይም መልዕክተኛን በመላክና በፈቃዱ የሚፈልገውን ነገር የሚያወርድለት እንጂ በገሀድ ሊያናግረው ተገቢው አይደለም። እርሱ የበላይ፤ ጥበበኛ ነውና።

وَكَذَٰلِكَ أَوْحَيْنَآ إِلَيْكَ رُوحًا مِّنْ أَمْرِنَا ۚ مَا كُنتَ تَدْرِى مَا ٱلْكِتَٰبُ وَلَا ٱلْإِيمَٰنُ وَلَٰكِن جَعَلْنَٰهُ نُورًا نَّهْدِى بِهِۦ مَن نَّشَآءُ مِنْ عِبَادِنَا ۚ وَإِنَّكَ لَتَهْدِىٓ إِلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٥٢﴾ صِرَٰطِ ٱللَّهِ ٱلَّذِى لَهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۗ أَلَآ إِلَى ٱللَّهِ تَصِيرُ ٱلْأُمُورُ ﴿٥٣﴾

**52-53.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልክ እንደዚሁ ወደ አንተ ከትዕዛዛችን ሲሆን ሂወትህ የሆነውን (ቁርዓን) አወረድነው። መጽሐፉም ሆነ እምነቱም ምን እንደሆነ የምታውቅ አልነበርክም። ግን ቁርአንን ከባሮቻችን የምንሻውን ሰው በእርሱ የምንመራበት ብርሃን አደረግነው። አንተም ወደ ቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ትመራለህ። ወደዚያ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የእርሱ ወደ ሆነው ወደ አላህ መንገድ (ትመራለህ)። ሙስሊሞች ሆይ! አስተውሉ። ነገሮች ሁሉ ወደ አላህ ብቻ ይመለሳሉ።

**ከምክክሩ ምዕራፍ ከአንቀፅ (31-53) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የትግዕስትን አስፈላጊነት፤
2. የትኛውም ችግር በወንጀል ምክንያት እንደሚደርስ፤
3. የሰው ልጅ የአላህን ቅጣት ሳያይ አላህን በትክክል እንደሚያውቅና እንደማይጠቅመው፤
4. የዱንያ ጥቅም ከአኼራ ጥቅም ጋር ሲነፃፀር ምንም እንደማይመስል፤
5. በኢስላም ምርጥ ሰው የሚባለው በእነዚህ አናቅፅ የተጠቀሱትን ባህሪያት ያሟላ መሆኑን፤
6. ግፈኛን መቅጣት ተገቢ ስለ መሆኑ፤
7. የተበደለ ሰው የበደሉን ያህል ቢወስድ ሁዱድ እስካልሆነ ድረስ እንደማያስቀጣው፤
8. በሙስሊሞች መካከል ይቅርታ መባባል ተገቢ ስለመሆኑ፤
9. ከተበደለ በኋላ ለራሱ የተበቀለን ሰው ለመቅጣት የሚያስቸል ህግ እንደሌለ፤
10. የትዕግስትን ትልቅነት መግለፅ፤
11. አላህ ላዘዘው ሁሉ ነገር ሰጥ ለጥ ብሎ መታዘዝ ግዴታ ስለመሆኑ፤
12. ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርጉ ሁሉ ለህዝቡ ማድረስ ያለባቸው አላህ ከባሮቹ ምን እንደሚፈልግ አብራርቶ መንገር መሆኑን፤
13. የሰው ልጅ በእምነት ከመገራቱ በፊት ምን እንደሚመስል፤
14. አላህ በዓለሙ ላይ እንደፈለገው የመጠቀም ስልጣን እንዳለው፤
15. በሴትም ሆነ በወንድ መካንነት ያለ መሆኑን፤
16. የውሃ አመጣጥ እንዴት እንደነበር መግለፅ፤
17. ቁርአን የሰዎች መንፈስ ሕይወት የሚሰራበት መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የምክክሩ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (43)
# የጌጣጌጥ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አዝዙኽሩፍ)

سُورَةُ الزُّخۡرُفِ

**በመካ የወረደ ምዕራፍ ነው። አናቅፁ (89) ናቸው።**
**የሱረቱ አዝ-ዙኽሩፍ መግቢያ**

ቁርኣንና ትልቅነቱን አውስቶ ከሓዲያን በአላህ መላዕክተኞች ላይ ያሳዩት የነበረውን ፌዝ ገልፆ በአላህ ማመን አስፈላጊ ለመሆኑ የሚያስረዱ ብዙ ማስረጃዎች ይደረድራል። ከሓዲያን ግን ለአላህ አጋሮች የሆኑ ሴት ልጆች እንዳሉት በጭፍኑ ሲከራከሩ ማስረጃ ሲያጡ አባቶቻቸው የነበሩበትን ላለመልቀቅ እንደሆነ ይገልፃል። የነብዩ ኢብራሒምን ታሪክ ያወሳና የመካ ከሓዲያን ብዙ ታላላቅ ሰዎች እያሉ በነብዩ (ﷺ) ላይ ቁርኣን መውረዱ በጣም እንዳራቃቸው ይናገራል። በመቀጠልም ሁሉም እንዳይከፍር ብሎ በሰፊው የፈለገውን ሁሉ የዱንያ መጠቃቀሚያ መስጠት እንደሚችል ያስታውሳል የሙሳንና የፊርዖንን ታሪክ ቀንጨብ በማድረግም ያወሳል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

حمٓ ﴿١﴾

**1.** ሓ፣ ሚይ ም፤*

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡمُبِينِ ﴿٢﴾ إِنَّا جَعَلۡنَٰهُ قُرۡءَٰنًا عَرَبِيّٗا لَّعَلَّكُمۡ تَعۡقِلُونَ ﴿٣﴾
وَإِنَّهُۥ فِيٓ أُمِّ ٱلۡكِتَٰبِ لَدَيۡنَا لَعَلِيٌّ حَكِيمٌ ﴿٤﴾ أَفَنَضۡرِبُ عَنكُمُ ٱلذِّكۡرَ صَفۡحًا أَن كُنتُمۡ
قَوۡمٗا مُّسۡرِفِينَ ﴿٥﴾

**2-5.** ገላጭ በሆነው መጽሐፍ እምላለሁ። (ዐረቦች ሆይ!) እኛ ታውቁ ዘንድ ቁርኣንን በዐረብኛ አደረግነው። እርሱም በመጽሐፎች እናት (መሰረት)* ውስጥ በእኛ ዘንድ እርግጥ ከፍተኛ ማዕረግ ያለውና በጥበብ የተሞላ ነው። ድንበር አላፊዎች ህዝቦች በመሆናችሁ ምክኒያት ቁርኣኑን ከማውረድ ከናንተ ማገድን እናግዳለን? (አናግድም)።

* ለውሃል መህፉዝ ለማለት ነው

وَكَمْ أَرْسَلْنَا مِن نَّبِيٍّ فِى ٱلْأَوَّلِينَ ﴿٦﴾ وَمَا يَأْتِيهِم مِّن نَّبِيٍّ إِلَّا كَانُوا۟ بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿٧﴾
فَأَهْلَكْنَآ أَشَدَّ مِنْهُم بَطْشًا وَمَضَىٰ مَثَلُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿٨﴾

**6-8.** በፊተኞችም ህዝቦች ውስጥ ከነብያት መካከል ብዙን ልከናል። ከነብይ አንድንም የሚመጣላቸው አልነበረም በእርሱ ይቀልዱበት (ያፌዙበት) የነበሩ ቢሆን እንጂ። ከእነርሱም በሀይል ይበልጥ የበረቱትን አጥፍተናል። የፊተኞችም አጠፋፍ ምሳሌ አልፏል።

وَلَئِن سَأَلْتَهُم مَّنْ خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ لَيَقُولُنَّ خَلَقَهُنَّ ٱلْعَزِيزُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٩﴾ ٱلَّذِى جَعَلَ
لَكُمُ ٱلْأَرْضَ مَهْدًا وَجَعَلَ لَكُمْ فِيهَا سُبُلًا لَّعَلَّكُمْ تَهْتَدُونَ ﴿١٠﴾ وَٱلَّذِى نَزَّلَ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءًۢ
بِقَدَرٍ فَأَنشَرْنَا بِهِۦ بَلْدَةً مَّيْتًا ۚ كَذَٰلِكَ تُخْرَجُونَ ﴿١١﴾ وَٱلَّذِى خَلَقَ ٱلْأَزْوَٰجَ كُلَّهَا وَجَعَلَ لَكُم مِّنَ
ٱلْفُلْكِ وَٱلْأَنْعَٰمِ مَا تَرْكَبُونَ ﴿١٢﴾ لِتَسْتَوُۥا۟ عَلَىٰ ظُهُورِهِۦ ثُمَّ تَذْكُرُوا۟ نِعْمَةَ رَبِّكُمْ إِذَا ٱسْتَوَيْتُمْ
عَلَيْهِ وَتَقُولُوا۟ سُبْحَٰنَ ٱلَّذِى سَخَّرَ لَنَا هَٰذَا وَمَا كُنَّا لَهُۥ مُقْرِنِينَ ﴿١٣﴾ وَإِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا لَمُنقَلِبُونَ ﴿١٤﴾

**9-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰማያትንና ምድርን ማን ፈጠራቸው ብለህ ብትጠይቃቸው ያ አሸናፊዉና አዋቂው ጌታ ነው የፈጠራቸው ይላሉ። አላህ ያ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ ያደረገላችሁ በእርሷም ውስጥ ትመሩ ዘንድ ለእናንተ መንገዶችን ያደረገላችሁ ነው። አላህ ከሰማይ ውሃን በልክ ያወረደላችሁ እና በእርሱም የሞተችውን አገር ህያው አደረግን። (ሰዎች ሆይ!) ልክ እንደዚሁ ከየመቃብሮቻችሁ ትውወጣላችሁ። ያም የፍጡር ዓይነቶችን ሁሉ (ሴቴና ወንዴ) አድርጎ የፈጠረ ለእናንተም ከመርከቦችና ከቤት እንሰሳዎች መካከል የምትጋልቧቸውን ያደረገላችሁ ነው። በጀርባዎቻቸው ላይ እንድትደላደሉ ከዚም በእርሱ ላይ በተደላደላችሁ ጊዜ የጌታችሁን ፀጋ እንድታስታውሱ፤ እንድትሉም ያ ይህንን የማንችለው ስንሆን ለእኛ የገራልን ጌታ ጥራት ተገባው። እኛ በእርግጥ ወደ ጌታችን አላህ ተመላሾች ነን እንድትሉ ነው።*

* ሙስሊም፤ አቡዳውድና ነሳኢ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) ፈረሳቸውን ሲጋልቡ (3) ጊዜ አሏህ አክበር፤ አሏህ አክበር፤ አሏህ አክበር ካሉ በኋላ ይህን የቁርኣን አንቀፅ ያነቡ ነበር። በመቀጠልም «አላሁ አክበር አላሁ አክበር አላሁ አክበር (ሱብሃነለዚ ሰኸረ ለና ሃዛ ወማ ኩናለሁ ሙቅርኒን ወኢና ኢላ ረቢና ለሙንቀሊቡን) አላሁመ ኢና ነሰአሉከ ፊሰፈሪና ሀዛ አልቢረ ወትተቅዋ ወሚነልዐመሊ ማተርዷ አላሁመ ሀዊን ዐለይና ሰፈረና ሃዛ ወጥዊ ዐና ቡዕደህ አላሁመ አንተ ሷሂቡ ፊሰፈር ወልኸሊፈቱ ፊልአህል አላሁመ ኢኒአዑዙ ቢከ ሚን ወዕሳኢ ሰፈር ወከኣበቲል መንዞር ወሱኢል ሙንቀለብ ፊልማሊ ወል አህል» ይሉ ነበር። (አሏህ አክበር ማለት አላህ የታላቆች ታላቅ ነው! አላህ የታላቆች ታላቅ ነው! አላህ የታላቆች ታላቅ ነው ማለት ነው) ይህን መጓጓዣ ያገራልን ጌታ ፍጹማዊ ነው። እኛ ይህን ለመፈፀም የምንችል አልነበርንም። የመጨረሻ መዳረሻችንም ወደ ጌታችን ነው።

አላህ ሆይ! በዚህ ጉዟችን መልካም መሥራትን (ቢር) ከመጥፎ መከልከልን (ተቅዋ) የምትወደውን ነገር እንድንፈፅምም እንጠይቅሃለን። አላህ ሆይ! ይህን ጉዞአችንን አመቻችልን፤ በአጭር ጊዜም የምንቆርጠው አድርገን። አላህ ሆይ! አንተ በጉዞ ላይ ጓደኛ (ባልደረባ) ነህ። የቤተሰብም ምትክ (ዋቢ) ነህ። አላህ ሆይ! እኔ ከጉዞ ጣጣ ከአመለካከት ለውጥና በንብረትና በቤተሰብ ላይ መጥፎ ነገር ደርሶ በመመለስ በአንተ እንበቃለሁ።) ከጉዞ ሲመለሱም የተጠቀሰውን ፀሎት ካነበቡ በኋላ ይህን ይበል። ኣይቡን ታኢቡን ዓቢዱን ሊረቢና ሃሚዱን» (ተውበት አድርገ፤ (አላህን) እየተገዛና ጌታችንን አመስጋኞች ሆነን ተመልሰናል።)

وَجَعَلُواْ لَهُۥ مِنۡ عِبَادِهِۦ جُزۡءًاۚ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَكَفُورٞ مُّبِينٌ ﴿١٥﴾ أَمِ ٱتَّخَذَ مِمَّا يَخۡلُقُ بَنَاتٖ
وَأَصۡفَىٰكُم بِٱلۡبَنِينَ ﴿١٦﴾ وَإِذَا بُشِّرَ أَحَدُهُم بِمَا ضَرَبَ لِلرَّحۡمَٰنِ مَثَلٗا ظَلَّ وَجۡهُهُۥ مُسۡوَدّٗا
وَهُوَ كَظِيمٌ ﴿١٧﴾ أَوَمَن يُنَشَّؤُاْ فِي ٱلۡحِلۡيَةِ وَهُوَ فِي ٱلۡخِصَامِ غَيۡرُ مُبِينٖ ﴿١٨﴾ وَجَعَلُواْ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ
ٱلَّذِينَ هُمۡ عِبَٰدُ ٱلرَّحۡمَٰنِ إِنَٰثًاۚ أَشَهِدُواْ خَلۡقَهُمۡۚ سَتُكۡتَبُ شَهَٰدَتُهُمۡ وَيُسۡـَٔلُونَ ﴿١٩﴾

**15-19.** ከባሮቹ መካከል ለእርሱ ቁራጭን (የተወሰነን) ብቻ አደረጉለት። ሰው ሲባል በእርግጥ ግልፅ ከሓዲ ነውና። አላህ ከሚፈጥረው ፍጡር መካከል ሴቶች ልጆችን ብቻ ለይቶ የራሱ ልጅ አድርጎ ያዝን? በወንዶች ልጆችም እናንተን መረጣችሁን? አንዳቸውም ለአልረህማን ምሳሌ ባደረገው ነገር በሴት ልጅ በተበሰረ ጊዜ እርሱ በቁጭት የተሞላ ሆኖ ፊቱ ጥቁር ይሆናል። በጌጣጌጥ ተከልሶ እንዲያድግ የሚደረገውን ክፍል እርሱም ከደካማነቱ የተነሳ በክርክር የማያብራራውን ፍጡር ሴትን ልጅ ብቻ ለይተው ለአላህ ያደርጋሉን? እነዚያን የአልረህማን ቅን ባሮች የሆኑትን መልአክትንም ሴቶች አደረጉ። ለመሆኑ እነርሱ መልአክት ሲፈጠሩ አብረው ነበሩን? መመስከራቸው በእርግጥ ትፃፋለች ስለ እሷም ይጠየቃሉ።

ከጌጣጌጥ (19) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት፡- አስመሳዮች አላህ ከጋኔን ጋር ተጋብቶ መላኢኮች ተገኙ በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

وَقَالُواْ لَوۡ شَآءَ ٱلرَّحۡمَٰنُ مَا عَبَدۡنَٰهُمۗ مَّا لَهُم بِذَٰلِكَ مِنۡ عِلۡمٍۖ إِنۡ هُمۡ إِلَّا يَخۡرُصُونَ ﴿٢٠﴾
أَمۡ ءَاتَيۡنَٰهُمۡ كِتَٰبٗا مِّن قَبۡلِهِۦ فَهُم بِهِۦ مُسۡتَمۡسِكُونَ ﴿٢١﴾ بَلۡ قَالُوٓاْ إِنَّا وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا
عَلَىٰٓ أُمَّةٖ وَإِنَّا عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِم مُّهۡتَدُونَ ﴿٢٢﴾ وَكَذَٰلِكَ مَآ أَرۡسَلۡنَا مِن قَبۡلِكَ فِي قَرۡيَةٖ مِّن نَّذِيرٍ
إِلَّا قَالَ مُتۡرَفُوهَآ إِنَّا وَجَدۡنَآ ءَابَآءَنَا عَلَىٰٓ أُمَّةٖ وَإِنَّا عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِم مُّقۡتَدُونَ ﴿٢٣﴾ ۞قَٰلَ أَوَلَوۡ
جِئۡتُكُم بِأَهۡدَىٰ مِمَّا وَجَدتُّمۡ عَلَيۡهِ ءَابَآءَكُمۡۖ قَالُوٓاْ إِنَّا بِمَآ أُرۡسِلۡتُم بِهِۦ كَٰفِرُونَ ﴿٢٤﴾
فَٱنتَقَمۡنَا مِنۡهُمۡۖ فَٱنظُرۡ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلۡمُكَذِّبِينَ ﴿٢٥﴾

**20-25.** አልረህማን በፈለገ ኖሮ ባልተገዛናቸው ነበር አሉ። ለእነርሱ በዚህ ምንም እውቀት የላቸውም፤ እነርሱ የሚዋሹ ህዝቦች እንጂ ሌላ አይደሉም። ከእርሱ (ከቁርኣን) በፊት መጽሐፍን ሰጠናቸውና ስለዚህ እነርሱ እሱን አጥብቀው የያዙ ናቸውን? ከቶውንም እኛ አባቶቻችንን በሃይማኖት ላይ አገኘናቸው። እኛም በፈለጎቻቸው ላይ ተመሪዎች ነን አሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ነገሩ ልክ እንደዚህ ነው። ከበፊትም በማንኛይቱም ከተማ ውስጥ አስፈራሪን አላክንም ቅምጥሎቹ እኛ አባቶቻችንን በሃይማኖት ላይ አገኘን። እኛም በፈለጎቻቸው ላይ ተከታዩች ነን ያሉ ቢሆኑ እንጂ። አስፈራሪው አባቶቻችሁን በእርሱ ላይ ካገኛችሁበት ይበልጥ ቀጥተኛን ሃይማኖት ባመጣላችሁም አላቸው። እኛ በእርሱ በተላካችሁበት ነገር (ሀይማኖት) ከሓዲያን ነን አሉ። ከእነርሱም ተበቀልን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያስተባባዩች መጨረሻ እንዴት እንደነበር ተመልከት።

وَإِذۡ قَالَ إِبۡرَٰهِيمُ لِأَبِيهِ وَقَوۡمِهِۦٓ إِنَّنِي بَرَآءٞ مِّمَّا تَعۡبُدُونَ ﴿٢٦﴾ إِلَّا ٱلَّذِي فَطَرَنِي فَإِنَّهُۥ سَيَهۡدِينِ ﴿٢٧﴾ وَجَعَلَهَا كَلِمَةَۢ بَاقِيَةٗ فِي عَقِبِهِۦ لَعَلَّهُمۡ يَرۡجِعُونَ ﴿٢٨﴾

**26-28.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ኢብራሂምም ለአባቱና ለህዝቦቹ እኔ ከምትገዙት ጣኦታት ሁሉ ንፁህ ነኝ። ከዚያ ከፈጠረኝ በስተቀር ማንንም አልገዛም። አላህንማ በእርግጥ ይመራኛልና ብቻውን አመልከዋለሁ ባለ ጊዜ (የነበረውን ሁኔታ አስታውስ)። በዝርዩች ውስጥ ወደ አላህ ይመለሱ ዘንድ (በአንድ አምላክ) ማመንን ቀሪ ቃል አደረጋት።

بَلۡ مَتَّعۡتُ هَٰٓؤُلَآءِ وَءَابَآءَهُمۡ حَتَّىٰ جَآءَهُمُ ٱلۡحَقُّ وَرَسُولٞ مُّبِينٞ ﴿٢٩﴾ وَلَمَّا جَآءَهُمُ ٱلۡحَقُّ قَالُواْ هَٰذَا سِحۡرٞ وَإِنَّا بِهِۦ كَٰفِرُونَ ﴿٣٠﴾ وَقَالُواْ لَوۡلَا نُزِّلَ هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانُ عَلَىٰ رَجُلٖ مِّنَ ٱلۡقَرۡيَتَيۡنِ عَظِيمٍ ﴿٣١﴾

**29-31.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይልቁን እነዚህን ቁረይሾችን አባቶቻቸውንም ቁርኣንንና ገላጭ መልዕክተኛ እስካመጣላቸው ድረስ አጣቀምኳቸው። እውነት በመጣላቸው ጊዜም ይህ ያመጣህው ድግምት ነው እኛም በእርሱ ከሓዲያን ነን አሉ። ይህም ቁርኣን በሁለት ከተሞች በአንዱ በሚኖር ታላቅ ሰው ላይ አይወርድም ኖሯልን? አሉ።

ከጌጣጌጥ ምዕራፍ (31) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዩኑስ አዙኹሩፍ ላይ እንዳለፈው ነብይነት የሚያስፈልግ በነበረ ስንት ሀብታሞች እያሉ ሙሐመድ መርጦ ለምን ላከ በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

أَهُمْ يَقْسِمُونَ رَحْمَتَ رَبِّكَۚ نَحْنُ قَسَمْنَا بَيْنَهُم مَّعِيشَتَهُمْ فِي ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَاۚ
وَرَفَعْنَا بَعْضَهُمْ فَوْقَ بَعْضٍ دَرَجَٰتٍ لِّيَتَّخِذَ بَعْضُهُم بَعْضًا سُخْرِيًّاۗ
وَرَحْمَتُ رَبِّكَ خَيْرٌ مِّمَّا يَجْمَعُونَ ﴿٣٢﴾

32. እነርሱ የጌታህን ስጦታ ያከፋፍላሉን? እኛ በቅርቢቱ ሕይወት እንኳን ኑሯቸውን በመካከላቸው አከፋፍለናል። ከፊላቸውም ከፊሉን ሰራተኛ አድርጎ ይይዝ ዘንድ ከፊላቸውን ከከፊሉ በላይ (በሀብት) አበለጥን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የጌታህም ፀጋ ገነት ከሚሰበስቡት ሀብት ሁሉ በላጭ ነው።

**ከጌጣጌጥ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-32) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በአላህ መማል ተገቢ ስለመሆኑ፤
2. የቁርአንን ትልቅነት፤
3. ሰዎች በሽርክ ተግባራቸው ምን እንደሚገጥማቸው ማስጠንቀቅ
4. ተውሒድን ማረጋገጥ፤
5. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት መረጋገጥ፤
6. የቁርአን ተኣምርነት እንማራለን።
7. ሰዎች በኢስላም ከመታነጻቸው በፊት የነበራቸውን ባህሪ መግለፅ፤
8. መጥፎ ነገሮችን ሸርዓው በሚፈቅደው መሰረት መቃወም ግዴታ ስለመሆኑ፤
9. የአረብ ዘላኞች ሴት ልጅን እንዴት ይጠሏት እንደነበር ማሳየት፤
10. የሴት ልጅ ጉድለት በጌጥ እንደሚጠገን፤
11. የሀሰት ምስክርነት የመሰከረ በአላህ ዘንድ ከፍተኛ ቅጣት እንደሚጠብቀው፤
12. ያለ ምንም እውቀት በአላህ ላይ መናገር ክልክል ስለመሆኑ፤
13. ማንንም ያለማስረጃ መቀበል እንደሌለብን፤
14. ከሰው ልጅ ብልሀትነት መለያዎች መካከል ትክክለኛን ነገር ህዝቡ ቢቃወመውም አጥብቆ መያዙ ነው።
15. ከሽርክና ከአሻራኪዎች ራስን ማፅዳት ግዴታ ስለመሆኑ፤
16. ልጆቹን መልካም ነገር አውርሶ የሄደ ሰው ያለው ምንዳ፤
17. አላህን በምንም ነገር የተቃወመ ሰው እንደሚከፍር፤
18. ማደህየትም ሆነ ማክበር ጤና ማድረግም ሆነ ማሳመም ብልህ ማድረግም ሆነ ሞኝ ማድረግ የራሱ የሆነ ምክንያት እንዳለው እንማራለን።

وَلَوْلَآ أَن يَكُونَ ٱلنَّاسُ أُمَّةً وَٰحِدَةً لَّجَعَلْنَا لِمَن يَكْفُرُ بِٱلرَّحْمَٰنِ لِبُيُوتِهِمْ سُقُفًا مِّن فِضَّةٍ
وَمَعَارِجَ عَلَيْهَا يَظْهَرُونَ ﴿٣٣﴾ وَلِبُيُوتِهِمْ أَبْوَٰبًا وَسُرُرًا عَلَيْهَا يَتَّكِـُٔونَ ﴿٣٤﴾ وَزُخْرُفًاۚ وَإِن
كُلُّ ذَٰلِكَ لَمَّا مَتَٰعُ ٱلْحَيَوٰةِ ٱلدُّنْيَاۚ وَٱلْـَٔاخِرَةُ عِندَ رَبِّكَ لِلْمُتَّقِينَ ﴿٣٥﴾

**33-35.** ሰዎች (በክህደት) ላይ አንድ ህዝብ የሚሆኑ ባልነበሩ ኖሮ በአልረህማ ለሚክዱ ሰዎች ሁሉ (በዚህች ዓለም) ለቤቶቻቸው የብር ጣራዎች፤ የሚወጣጡባቸው የብር መሰላሎችና፤ የቤቶቻቸው የብር በሮች፤ በእነርሱ ላይ የሚደገፉባቸውም የብር አልጋዎች እና የወርቅ ጌጥንም ባደረግንላቸው ነበር። ይህም ሁሉ የቅርቢቱ ሕይወት መጣቀሚያ እንጂ ሌላ አይደለም። ጠፊ ነው። መጨረሻይቱም አገር በጌታህ ዘንድ ለጥንቁቆች ብቻ ናት።

وَمَن يَعْشُ عَن ذِكْرِ ٱلرَّحْمَٰنِ نُقَيِّضْ لَهُۥ شَيْطَٰنًا فَهُوَ لَهُۥ قَرِينٌ ﴿٣٦﴾ وَإِنَّهُمْ لَيَصُدُّونَهُمْ عَنِ ٱلسَّبِيلِ وَيَحْسَبُونَ أَنَّهُم مُّهْتَدُونَ ﴿٣٧﴾ حَتَّىٰٓ إِذَا جَآءَنَا قَالَ يَٰلَيْتَ بَيْنِى وَبَيْنَكَ بُعْدَ ٱلْمَشْرِقَيْنِ فَبِئْسَ ٱلْقَرِينُ ﴿٣٨﴾ وَلَن يَنفَعَكُمُ ٱلْيَوْمَ إِذ ظَّلَمْتُمْ أَنَّكُمْ فِى ٱلْعَذَابِ مُشْتَرِكُونَ ﴿٣٩﴾

**36-39.** (በቁርኣን ከተወሳው) ከአልረህማ ግሳጼ (ከቁርኣን) የሚደናበርም ሰው ለእርሱ ሰይጣንን እናስጠጋለን ስለዚህ እርሱ ለእርሱ የሁልግዜ ቁራኛው ነው። እነሱም (ተደናባሪዎች) ሁሉ ወደ ትክክለኛው መንገድ ተመሪዎች መሆናቸውን የሚያስቡ ሲሆኑ ሰይጣናት ከቀጥተኛው መንገድ በእርግጥ ያግዷቸዋል። (በትንሳኤ) ወደ እኛ በመጣ ጊዜ (ቁራኛዬ ሆይ) በእኔና ባንተ መካከል የምስራቅና የምዕራብ ርቀት በኖረ ዋ ምኞቴ ምን የከፋ ቁራኛ ነህ ይላል። (ከሓዲያን ሆይ)፣ ስለ በደላችሁም ዛሬ እናንተ በቅጣት ተጋሪዎች መሆናችሁ አይጠቅማችሁም ይባላሉ።

ከጌጣጌጥ (36) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ወሊድ ቢን ሙጊራ ሙሐመድ የሚለው ነገር እውነት ቢሆን ኖሮ በእኔ ወይም በዑርዋህ ቢን መስዑድ አስቀፊይ ላይ በወረደ ነበር በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

أَفَأَنتَ تُسْمِعُ ٱلصُّمَّ أَوْ تَهْدِى ٱلْعُمْىَ وَمَن كَانَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٤٠﴾ فَإِمَّا نَذْهَبَنَّ بِكَ فَإِنَّا مِنْهُم مُّنتَقِمُونَ ﴿٤١﴾ أَوْ نُرِيَنَّكَ ٱلَّذِى وَعَدْنَٰهُمْ فَإِنَّا عَلَيْهِم مُّقْتَدِرُونَ ﴿٤٢﴾ فَٱسْتَمْسِكْ بِٱلَّذِىٓ أُوحِىَ إِلَيْكَ ۖ إِنَّكَ عَلَىٰ صِرَٰطٍ مُّسْتَقِيمٍ ﴿٤٣﴾ وَإِنَّهُۥ لَذِكْرٌ لَّكَ وَلِقَوْمِكَ ۖ وَسَوْفَ تُسْـَٔلُونَ ﴿٤٤﴾ وَسْـَٔلْ مَنْ أَرْسَلْنَا مِن قَبْلِكَ مِن رُّسُلِنَآ أَجَعَلْنَا مِن دُونِ ٱلرَّحْمَٰنِ ءَالِهَةً يُعْبَدُونَ ﴿٤٥﴾

**40-45.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ ደንቆሮዎችን ታሰማለህን? ወይ እውሮችንና በግልፅ ጥመት ውስጥ የሆኑ ሰዎችን ትመራለህን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተንም ቅጣታቸውን ሳታይ ብንወስድህ እኛ ከእነርሱ ተበቃዩች ነን ወይም ያንን የቀጠርናቸውን ብናሳይህ እኛ ከእነርሱ ቅጣት ላይ ቻይዎች ነን። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያንንም

ወደ አንተ የተወረደልህን አጥብቀህ ያዝ። አንተ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ነህና። (ሙሐመድ ሆይ) እርሱም (ቁርኣን) ለአንተም ሆነ ለህዝቦችህ ታላቅ ክብር ነው። ወደ ፊትም ከርሱ ትጠየቃላችሁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመልዕክተኞችም ከአንተ በፊት የላክናቸው ተከታዩቻቸውን ከአልረህማን ሌላ የሚገዙዋቸው የሆኑን አማልክት አድርገው እንደ ሆነ ጠይቃቸው።

وَلَقَدْ أَرْسَلْنَا مُوسَىٰ بِـَٔايَٰتِنَآ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ وَمَلَإِيْهِۦ فَقَالَ إِنِّى رَسُولُ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٤٦﴾ فَلَمَّا
جَآءَهُم بِـَٔايَٰتِنَآ إِذَا هُم مِّنْهَا يَضْحَكُونَ ﴿٤٧﴾ وَمَا نُرِيهِم مِّنْ ءَايَةٍ إِلَّا هِىَ أَكْبَرُ مِنْ أُخْتِهَا ۖ
وَأَخَذْنَٰهُم بِٱلْعَذَابِ لَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ﴿٤٨﴾ وَقَالُوا۟ يَٰٓأَيُّهَ ٱلسَّاحِرُ ٱدْعُ لَنَا رَبَّكَ بِمَا عَهِدَ عِندَكَ
إِنَّنَا لَمُهْتَدُونَ ﴿٤٩﴾ فَلَمَّا كَشَفْنَا عَنْهُمُ ٱلْعَذَابَ إِذَا هُمْ يَنكُثُونَ ﴿٥٠﴾ وَنَادَىٰ فِرْعَوْنُ فِى قَوْمِهِۦ
قَالَ يَٰقَوْمِ أَلَيْسَ لِى مُلْكُ مِصْرَ وَهَٰذِهِ ٱلْأَنْهَٰرُ تَجْرِى مِن تَحْتِىٓ ۖ أَفَلَا تُبْصِرُونَ ﴿٥١﴾ أَمْ أَنَا۠ خَيْرٌ
مِّنْ هَٰذَا ٱلَّذِى هُوَ مَهِينٌ وَلَا يَكَادُ يُبِينُ ﴿٥٢﴾ فَلَوْلَآ أُلْقِىَ عَلَيْهِ أَسْوِرَةٌ مِّن ذَهَبٍ أَوْ جَآءَ
مَعَهُ ٱلْمَلَٰٓئِكَةُ مُقْتَرِنِينَ ﴿٥٣﴾ فَٱسْتَخَفَّ قَوْمَهُۥ فَأَطَاعُوهُ ۚ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ قَوْمًا فَٰسِقِينَ ﴿٥٤﴾ فَلَمَّآ
ءَاسَفُونَا ٱنتَقَمْنَا مِنْهُمْ فَأَغْرَقْنَٰهُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٥٥﴾ فَجَعَلْنَٰهُمْ سَلَفًا وَمَثَلًا لِّلْءَاخِرِينَ ﴿٥٦﴾

**46-56.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳንም በታዐምራቶቻችን ወደ ፈርዖንና ወደ ሹማምንቶች በእርግጥ ላከን እና የዓለማት ጌታ መልዕክተኛ ነኝ አላቸውም። በታዐምራታችንም በመጣባቸው ጊዜ ወዲያውኑ እነርሱ በእርሷ ይስቃሉ። ከተዐምራት አንዲትንም እናሳያቸውም እርሷ ከብጤዋ በጣም የበለጠች ብትሆን እንጅ ከክህደታቸው ይመለሱም ዘንድ በቅጣት ያዝናቸው። አንተ ድግምተኛ አዋቂ ነህ! ጌታህን አንተ ዘንድ ቃል በገባልህ ለእኛ ለምንልን እኛ ቅጣቱን ቢያነሳልን ተመሪዎች ነን አሉም። ስቃዩን ከእነርሱ ላይ በገለጥንም ጊዜ ወዲያውኑ ቃልኪዳናቸውን ያፈርሳሉ። ፈርዖን በህዝቦቹ ውስጥ ተጣራ፤ ህዝቦች ሆይ! የመስር (ግብጽ) ግዛት የእኔ አይደለምን?አለ። እነዚህም ጅረቶች ከስሬ የሚፈሱ ሲሆኑ የእኔ አይደሉምን? አትመለከቱምን? በእውነት እኔ ከዚህ ያ እርሱ ወራዳ ጉዳዩንም በደንብ ሊገልፅ የማይችል ከሆነው ሰው በላጭ ነኝ። በእርሱ ላይ የወርቅ አንባሮች ለምን አልተጣሉበትም ወይም መላዕክት ከርሱ ጋር ተቆራኝተው ለምን አልመጡም አለ። ህዝቦችንም አቄላቸው፤ ታዘዙትም እነርሱም አመፀኞች ህዝቦች ነበሩና። ባስቆጡንም ጊዜ ከእነርሱ ተበቀልን ሁሉንም አሰመጥናቸው። በጥፋት ቀዳሚዎችና ለኋለኞች መቀጣጫ ምሳሌም አደረግናቸው።

۞ وَلَمَّا ضُرِبَ ٱبۡنُ مَرۡيَمَ مَثَلًا إِذَا قَوۡمُكَ مِنۡهُ يَصِدُّونَ ﴿٥٧﴾ وَقَالُوٓاْ ءَأَٰلِهَتُنَا خَيۡرٌ أَمۡ هُوَۚ
مَا ضَرَبُوهُ لَكَ إِلَّا جَدَلَۢاۚ بَلۡ هُمۡ قَوۡمٌ خَصِمُونَ ﴿٥٨﴾ إِنۡ هُوَ إِلَّا عَبۡدٌ أَنۡعَمۡنَا عَلَيۡهِ
وَجَعَلۡنَٰهُ مَثَلًا لِّبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ﴿٥٩﴾ وَلَوۡ نَشَآءُ لَجَعَلۡنَا مِنكُم مَّلَٰٓئِكَةً فِي ٱلۡأَرۡضِ
يَخۡلُفُونَ ﴿٦٠﴾ وَإِنَّهُۥ لَعِلۡمٌ لِّلسَّاعَةِ فَلَا تَمۡتَرُنَّ بِهَا وَٱتَّبِعُونِۚ هَٰذَا صِرَٰطٌ مُّسۡتَقِيمٌ ﴿٦١﴾
وَلَا يَصُدَّنَّكُمُ ٱلشَّيۡطَٰنُۖ إِنَّهُۥ لَكُمۡ عَدُوٌّ مُّبِينٌ ﴿٦٢﴾

**57-62.** የመርየም ልጅ ዒሳ ምሳሌ በተደረገ ጊዜ ከሓዲያን ህዝቦችህ ወዲያውኑ ከእርሱ ሌሎችን ይስቃሉ (ይንጫጫሉ)። አማልክቶቻችን ይበልጣሉን? ወይስ እርሱ ይበልጣል አሉም። ለክርክርም እንጅ ላንተ እርሱ ምሳሌ አላደረጉትም። በእውነት እነርሱ ክርክረ ብርቱ ህዝቦች ናቸው። እርሱ (ዒሳ) በእርሱ ላይ የለገስለት ለኢስራኤል ልጆች ተዐምር ያደረግነው አገልጋይ ባሪያችን እንጂ ሌላ አይደለም። ብንፈልግም ኖሮ በምድር ላይ በእናንተ ምትክ መላዕክትን ባደረግን ነበር። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እርሱም (ኢሳ) ለሰዓቲቱ ማወቂያ በእርግጥ ምልክት ነው። በእርሷም አትጠራጠሩ። ተከተሉኝም። ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው (በላቸው)። ሰይጣንም አያግዳችሁ። እርሱ ለእናንተ ግልፅ ጠላት ነውና።

ከጌጣጌጥ ምዕራፍ (57) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-

(ሀ) ነብዩ (ﷺ) በቁረይሾች ከአላህ ሌላ የሚመለክ ሰው ምንም ኸይር የለውም ሲሏቸው ዒሳ ነብይ ነው ትል የለምን? ዒሳ ደግሞ እንደኛ ጣኦቶችን አመልኳል በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ።)

(ለ) መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ከመልዕክተኞችም ከአንተ በፊት የላክናቸው ተከታዮቻቸውን ከአልረህማን ሌላ የሚገዙዋቸው የሆንን አማልክት አድርገው እንደ ሆነ ጠይቃቸው። አዝ-ዙኹሩፍ 45 የሚለው የቁርኣን አያ ሲወርድ ይህ በወረደ ጊዜ ከሓዲያን የዒሳን መወሳት አንስተው ሙሐመድ እኮ የሚፈልገው ክርስቲያኖች ዒሳን አምላክ አድርገው እንደያዙ ሁሉ እሱንም አምላክ አድርገኝ እንድንይዘው ነው በማለታቸው ነው።

(ሐ) ብዙ የተፍሲር ምሁራን እንደሚሉት ኢብኑ ዚባራዕ የሚባል ሰውየ ከመስለሙ በፊት ከሓዲያን ሆይ! እናንተና ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ጣዖታት የገሀነም ማገዶዎች ናችሁ። እናንተ ለእርሷ ወራጆች ናችሁ።»አንቢያ (98) የሚለው የቁርኣን አንቀፅ ሲወርድ ኢብኑ ዚባራዕ በካዕባ ጌታ ይንብኝ አሸንፌሃለሁ አለ። ክርስቲያኖች ዒሳን ይገዙ የለም፤ አይሁዶች ኡዘይርን፤ በኑመለይኽ መላኢኮችን ያመልኩ የለም አንተ እንደምትለው እነዚህ ሁሉ እሳት የሚገቡ ከሆነ እኛም ከአማልዕክቶቻችን ጋር ብንገባ አይከፋንም ሲላቸው ነብዩ (ﷺ) የቤተሰቦችህን ቋንቋ እንኳ አታውቅምን ማ የሚለው ቃል ለምን አገልግሎት እንደሚውል አታውቅም በማለት ሲመልሱለት ነው የወረደው።

وَلَمَّا جَآءَ عِيسَىٰ بِٱلۡبَيِّنَٰتِ قَالَ قَدۡ جِئۡتُكُم بِٱلۡحِكۡمَةِ وَلِأُبَيِّنَ لَكُم بَعۡضَ ٱلَّذِي
تَخۡتَلِفُونَ فِيهِۖ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُونِ ﴿٦٣﴾ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ رَبِّي وَرَبُّكُمۡ فَٱعۡبُدُوهُۚ هَٰذَا صِرَٰطٞ
مُّسۡتَقِيمٞ ﴿٦٤﴾ فَٱخۡتَلَفَ ٱلۡأَحۡزَابُ مِنۢ بَيۡنِهِمۡۖ فَوَيۡلٞ لِّلَّذِينَ ظَلَمُواْ مِنۡ عَذَابِ يَوۡمٍ أَلِيمٍ ﴿٦٥﴾
هَلۡ يَنظُرُونَ إِلَّا ٱلسَّاعَةَ أَن تَأۡتِيَهُم بَغۡتَةٗ وَهُمۡ لَا يَشۡعُرُونَ ﴿٦٦﴾ ٱلۡأَخِلَّآءُ يَوۡمَئِذِۭ بَعۡضُهُمۡ
لِبَعۡضٍ عَدُوٌّ إِلَّا ٱلۡمُتَّقِينَ ﴿٦٧﴾

**63-67.** ዒሳ ተዐምራቶቻችን ይዞ በመጣ ጊዜ በእርግጥ በጥበብ መጣሁላችሁ፡፡ የዚያንም የምትለያዩበትን ጉዳይ ከፊሉን ለእናንተ ላብራራላችሁ መጣሁ፡፡ እናም አላህን ፍሩ ታዘዙኝም፡፡ አላህ ጌታዬ ጌታችሁም ነው፡፡ እናም በብቸኝነት ተገዙት፡፡ ይህ ቀጥተኛ መንገድ ነው፡፡ ከመካከላቸውም አህዛቦች ተለያዩ፡፡ ለእነዚያም ለበደሉት ህዝቦች ከአሳማሚ ቀን ቅጣት ወዩላቸው፡፡ ሰዓቲቱን እነርሱ የማያውቁ ሆነው በድንገት ልትመጣላቸው እንጅ ሌላን ነገር ይጠባበቃሉ፡፡ አላህን የሚፈሩ ሰዎች ብቻ ሲቀሩ ወዳጆች በዚያ ቀን ከፊላቸው ለከፊሉ ጠላት ነው፡፡

يَٰعِبَادِ لَا خَوۡفٌ عَلَيۡكُمُ ٱلۡيَوۡمَ وَلَآ أَنتُمۡ تَحۡزَنُونَ ﴿٦٨﴾ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ بِـَٔايَٰتِنَا وَكَانُواْ
مُسۡلِمِينَ ﴿٦٩﴾ ٱدۡخُلُواْ ٱلۡجَنَّةَ أَنتُمۡ وَأَزۡوَٰجُكُمۡ تُحۡبَرُونَ ﴿٧٠﴾ يُطَافُ عَلَيۡهِم بِصِحَافٖ مِّن
ذَهَبٖ وَأَكۡوَابٖۖ وَفِيهَا مَا تَشۡتَهِيهِ ٱلۡأَنفُسُ وَتَلَذُّ ٱلۡأَعۡيُنُۖ وَأَنتُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ﴿٧١﴾ وَتِلۡكَ
ٱلۡجَنَّةُ ٱلَّتِيٓ أُورِثۡتُمُوهَا بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٧٢﴾ لَكُمۡ فِيهَا فَٰكِهَةٞ كَثِيرَةٞ مِّنۡهَا تَأۡكُلُونَ ﴿٧٣﴾

**68-73.** ባሮቼ ሆይ! ዛሬ ቀን በእናንተ ላይ ምንም ፍርሀት የለባችሁም፡፡ እናንተም የምታዝኑ አይደላችሁም ይባላሉ፡፡ እነዚያ በአንቀፆቻችን ያመኑና ፍፁም ታዛዦች የነበሩ፡፡ ባሮቼ ሆይ! ገነትን ግቡ፡፡ እናንተም ሚስቶቻችሁም ትደሰታላችሁ፡፡ ትከበራላችሁም ይባላሉ፡፡ ከወርቅ የሆኑ ሰፋፊ ዝርግ ሳህኖችና ኩባያዎች በእነርሱ ላይ ይዝዞራሉ፡፡ በእርሷም ውስጥ ነፍሶች የሚከጅሉት ዓይኖችም የሚደሰቱበት ሁሉ አለ፡፡ እናንተም በውስጧ ዘላለም ዘወታሪዎች ናችሁ፡፡ ይህም ያ ትሰሩት በነበራችሁት ዋጋ የተሰጣችሁት ገነት ነው፡፡ ለእናንተ በውስጧ ብዙ ፍራፍሬዎች አሏችሁና ከእርሷ እንደልባችሁ ትበላላችሁ ይባላሉ፡፡

إِنَّ ٱلْمُجْرِمِينَ فِى عَذَابِ جَهَنَّمَ خَٰلِدُونَ ﴿٧٤﴾ لَا يُفَتَّرُ عَنْهُمْ وَهُمْ فِيهِ مُبْلِسُونَ ﴿٧٥﴾ وَمَا ظَلَمْنَٰهُمْ وَلَٰكِن كَانُوا۟ هُمُ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٧٦﴾ وَنَادَوْا۟ يَٰمَٰلِكُ لِيَقْضِ عَلَيْنَا رَبُّكَ ۖ قَالَ إِنَّكُم مَّٰكِثُونَ ﴿٧٧﴾ لَقَدْ جِئْنَٰكُم بِٱلْحَقِّ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَكُمْ لِلْحَقِّ كَٰرِهُونَ ﴿٧٨﴾

**74-78.** አመፀኞች በገሀነም ስቃይ ውስጥ በእርግጥ ዘወታሪዎች ናቸው። ከእነርሱም ቅጣት በፍፁም አይቃለልላቸውም። እነርሱም በእርሱ ውስጥ ተስፋ ቆራጮች ናቸው። አልበደልናቸውም። ግን በዳዩች እነርሱው ብቻ ነበሩ። ማሊክ ሆይ፤ ጌታህ በእኛ ላይ (በሞት) ይፍረድ እያሉ። ይጣራሉም። እናንተ (በቅጣት ውስጥ) ለዘላለም ነዋሪዎች ናችሁ ይላቸዋል። እውነተኛውን መንገድ በእርግጥ አመጣንላችሁ ግን አብዛሀኞቻቸው እውነትን ጠይዎች ነበራችሁ ይባላሉ።

أَمْ أَبْرَمُوٓا۟ أَمْرًا فَإِنَّا مُبْرِمُونَ ﴿٧٩﴾ أَمْ يَحْسَبُونَ أَنَّا لَا نَسْمَعُ سِرَّهُمْ وَنَجْوَىٰهُم ۚ بَلَىٰ وَرُسُلُنَا لَدَيْهِمْ يَكْتُبُونَ ﴿٨٠﴾

**79-80.** ይልቁንም (በነብዩ ላይ በማደም) ነገርን አጠነከሩን? እኛም ተንኮላቸውን ወደ እነርሱ በመመለስ አጠንካሪዎች ነን። ወይም እኛ ሚስጥራቸውንና ውይይታቸውን የማንሰማ መሆናችንን ያስባሉን? ነገሩ እነርሱ እንደሚሉት አይደለም። መልዕክተኞችን እነርሱ ዘንድ ናቸው የሚሉትን ሁሉ ይፅፋሉ።

قُلْ إِن كَانَ لِلرَّحْمَٰنِ وَلَدٌ فَأَنَا۠ أَوَّلُ ٱلْعَٰبِدِينَ ﴿٨١﴾ سُبْحَٰنَ رَبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ رَبِّ ٱلْعَرْشِ عَمَّا يَصِفُونَ ﴿٨٢﴾

**81-82.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለአልረሀማን ልጅ የለውም እንጂ ቢኖረው እኔ ለልጁ የተገዢዎች መጀመሪያ ነኝ በላቸው። የሰማያት፤ የምድርና የዙፋኑ ጌታ ከሓዲያን ስለ እሱ ከሚሉት ነገር ሁሉ ጠራ።

فَذَرْهُمْ يَخُوضُوا۟ وَيَلْعَبُوا۟ حَتَّىٰ يُلَٰقُوا۟ يَوْمَهُمُ ٱلَّذِى يُوعَدُونَ ﴿٨٣﴾ وَهُوَ ٱلَّذِى فِى ٱلسَّمَآءِ إِلَٰهٌ وَفِى ٱلْأَرْضِ إِلَٰهٌ ۚ وَهُوَ ٱلْحَكِيمُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٨٤﴾

**83-84.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተዋቸው። ያንን ያስፈራሩበት የነበሩትን ቀናቸውን እስከሚገናኙ ድረስ በስህተታቸው (ውስጥ) ይዋኙ። እርሱ ያ! በሰማይ ውስጥ ሊገዙት የሚገባው በምድርም ውስጥ ሊገዙት የሚገባው ብቸኛ አምላክ ነው። እርሱ ጥበበኛ፤ አዋቂ ነው።

وَتَبَارَكَ ٱلَّذِي لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا وَعِندَهُۥ عِلۡمُ ٱلسَّاعَةِ وَإِلَيۡهِ تُرۡجَعُونَ ﴿٨٥﴾

**85.** ያም የሰማያት፤ የምድርና በመካከላቸው ያለው ሁሉ ንግስና ለእርሱ ብቻ የሆነው አምላክ ላቀ። የሰዓቲቱም የመምጫዋ ዘመን ዕውቀት በእርሱ ዘንድ ብቻ ነው። ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ።

وَلَا يَمۡلِكُ ٱلَّذِينَ يَدۡعُونَ مِن دُونِهِ ٱلشَّفَٰعَةَ إِلَّا مَن شَهِدَ بِٱلۡحَقِّ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ﴿٨٦﴾ وَلَئِن سَأَلۡتَهُم مَّنۡ خَلَقَهُمۡ لَيَقُولُنَّ ٱللَّهُۖ فَأَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ﴿٨٧﴾

**86-87.** እነዚያ ከአላህ ሌላ የሚገዟቸው አማልክት ሁሉ እነሱ ትክክለኛውን የሚያውቁ ሆነው በእውነት ከመሰከሩት ክፍሎች በስተቀር ምልጃ አይችሉም። ማን እንደ ፈጠራቸው ብትጠይቃቸው በእርግጥ አላህ ነው ይላሉ። ታዲያ (ከትክክለኛው እምነት) ወዴት ይዞራሉ።

وَقِيلِهِۦ يَٰرَبِّ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ قَوۡمٞ لَّا يُؤۡمِنُونَ ﴿٨٨﴾ فَٱصۡفَحۡ عَنۡهُمۡ وَقُلۡ سَلَٰمٞۚ فَسَوۡفَ يَعۡلَمُونَ ﴿٨٩﴾

**88-89.** (ነብዩ) ጌታዬ ሆይ፣ እነዚህ የማያምኑ ህዝቦች ናቸው ማለቱም። (እውቀቱ አላህ ዘንድ ነው) (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነርሱን ተዋቸው። ነገሬ ሰላም ነው በልም። ወደፊትም የሚመጣባቸውን ሲደርስ ያውቃሉ።

**ከጌጣጌጥ ምዕራፉ ከአንቀፅ (33-89) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የሰው ልጅ ወደ ዱንያ መዘንበሉ የተፈጥሮ ዝንባሌ ስለመሆኑና ከሃዲ በክህደቱ ምክንያት ዱንያ የሚሰጠው ቢሆን ኖሮ ሁሉም ሰው ዱንያን ለማግኘት በካደ ነበር፤
2. ዱንያ በአላህ ዘንድ ምን ያህል የተናቀችና የተዋረደች እንደሆነች፤ አኼራ ለፈሪሀኖች የተሸለ መሆኑን
3. የአላህን ህግ ያልተቀበሉ ሰዎች ሰይጣን እንደሚዘጋጅላቸውና ሁልጊዜም ቀናን መንገድ እንዳይከተሉ ማድረጋቸው፤
4. የቂያማ ቀን ቅጣት ሰዎች በመብዛታቸው የማይቃለል መሆኑ፤
5. አላህ አይኑን ያጠፋውና ጆሮውን ያደነቆው ማንም ቀናውን መንገድ ሊመራው እንደማይችል፤
6. በየጊዜው በነበሩ ህዝቦች ዘንድ የነበሩ ነብያትን ሲያስወጧቸው ልበቀልላቸው እንደነበር፤
7. አላህ ለመልዕክተኛው ነብዩ (ﷺ) የገባውን ቃል ኪዳን ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በተግባር ማሳየቱ፤
8. በቁርኣን ሐዲስ መመራት ግድ ስለመሆኑ፤
9. የዚህች ኡመት ክብር በቁርኣን እንደሆነና ቁርኣንን ከተወች አላህ እንደሚያዋርዳት፤
10. ተዓምሮችን ላመጣላቸው ሰው እውነተኝነት ማስረጃ ቢሆኑም ያያት ሁሉ ግን ያምናል ማለት እንዳልሆነ፤

11. አላህ ግለሰቦችንም ሆነ ህዝቦችን ከአንድ ጊዜም አልፎ በተደጋጋሚ ይቶብቱ በወንጀላቸው ሊቀጣቸው እንደሚችል፤
12. ቃል ኪዳንን ማፍረስ ክልክል ስለመሆኑና ከንፍቅና ባህሪያቶችና ምልክቶች ስለመሆኑናቸው
13. ኩራትን ማውገዝ፤
14. ድሆችንና ሚስኪኖችን መናቅ የግፈኞች ባህሪ መሆኑ፤
15. ከአላህ ቁጣ ማስጠንቀቅን፤
16. ቁረይሾች ተሚጋቾች እንደነበሩ፤
17. ሀቅን ለማረጋገጥ ውሸትን ለማጋለጥ ካልሆነ በስተቀር መከራከር አግባብ እንዳልሆነ፤
18. የነብዩ ዒሳ ትልቅነትና የነብዩ ኢሳ ወደ መሬት መውረድ ከትንሳኤ ታላላቅ ምልክቶች አንዱ ስለመሆኑ፤
19. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
20. ሰይጣንን መከተል ክልክል ስለመሆኑ፤
21. ነብዩ ዒሳ ወደ በኒ ኢስራኢሎች የተላኩ ስለመሆናቸው፤
22. አላህን መፍራትና ነብዩን መታዘዝ ግዴታ ስለመሆኑ፤
23. ጭቅጭቅ ሊያስከትል የሚችለውን መጥፎ ነገር ማስጠንቀቅ፤
24. አላህ ለአይሁድና ለነሷራ ኢስላምን ላለመቀበላቸው ምክንያት የአይቀጡ ቅጣት ዛቻ፤
25. ለአላህ ያልሆኑ ወዳጅነቶች ሁሉ የትንሳኤ ቀን እንደሚቆራረጡ፤
26. አላህን መፍራት ያለው ክብር፤
27. ሙስሊም የሆነ ሰው ከሙስሊም ሚስቱ ጋር በጀነት እንደሚገናኝ፤
28. የጀነትን ምግቦችና ፀጋዋች በጥቂቱ፤
29. እምነት መልካም ስራ ለጀነት ምክንያት እንደሆነ ሁሉ ሽርክና ወንጀሎችን ለእሳት ምክንያቶች እንደሆኑ፤
30. በሽርክና በወንጀል ነፍሱን ያቆሸሸ ሰው ቅጣቱ ምን እንደሆነ ማስታወስ፤
31. የአኼራ ቅጣት እንደማይቻልና ከባድ እንደሆነ፤
32. እውነትን ለመጥላት ከሚገፋፉ ምክንያቶች ዋናው የዚህችን ዓለም ደስታና ፌሽታ መውደድ መሆኑን፤
33. ሰዎችን ሲያናግሩ ለስለስ አድርጎ ማናገር እንደአቅማቸው የሚመጥናቸውን ማቅረብ፤
34. አጋሪዎችን በቂያማ ቀን ቅጣት መዛት፤
35. አላህ ልጅ አለው የሚሉትን ሰዎች አባባላቸውን ውድቅ የሚያደርጉ ማስረጃዎችን ማቅረብ፤
36. ሰዎች መመስከር ያለባቸው በሚያውቁት እንጂ በማያውቁት ነገር ፈፅሞ መናገር እንደሌለባቸው፤
37. የትንሳኤ ቀን ሽምግልና ካለ አላህ ማንንም እንደማይችል፤
38. የአረብ አጋሪዎች በአምልኮት እንጂ በጌትነቱ ያጋሩ እንደነበር፤
39. ህግጋቶችን መተግበር ባልተቻለበት ጊዜ ይቅርታ ማለት ተገቢ እንደሆነ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የጌጣጌጥ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (44)
## የጭስ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አድዱኻን)

سُورَةُ الدُّخَانِ

### የወረደውበመካነው። የአናቅ ፁ ብዛት (59) ናቸው።
### የሱረቱ አድ-ዱኻን መግቢያ

ታላቁ ቁርኣን በለይለተልቀድር ከአላህ የወረደ መሆኑ ሙቶ መነሳት አለ የማይባል ሀቅ መሆኑን ያስተምርና ሙቶ መነሳትን ለሚቃወሙ ሁሉ ይከራከራል። በተጨማሪም መኮችን ከቀደምት ከሓዲያን የፊርአውን ሰዎች ጋር አነፃፅሮ በእነሱ ላይ የደረሰው ቅጣትና የተወሰዱ እርምጃዎች ምን ምን እንደሆኑ ይገልፃል። ከዚያ የክህደት ቡድኖች ሁሉ ቀጠሮዋቸው ቂያማ ቀን መሆኑንና የአማኞችም ሆነ የከሓዲያን ምንዳ ምን እንደሚመስል በግልፅ ያስቀምጣል። ወደ መጨረሻም በመጀመሪያ ያነሳውን አንቀፅ የቁርኣን ትልቅነት አውስቶ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተልዕኮ ያስተባበሉ ሁሉ አላህ ቁጣውን ሊያወርድባቸው እንደሚችል በማስፈራራት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

ካለፈው ምዕራፍ ጋር የከበደና የጠበቀ ግንኙነት ነው ያለው። በተለይም፤

1. ያለፈው ምዕራፍ ያከተመው በዛቻ ሲሆን ይህም ምዕራፍ የጀመረው በማስፋራራት መሆኑ
2. ባለፈው ምዕራፍ ነብዩ (ﷺ) ጌታዬ...ማለታቸውን አውስቶዋል። በዚህኛው ምዕራፍ ደግሞ ነብዩ ሙሳ (ﷺ) ... ማለታቸውን ያስታውሳል
3. በፊተኛው ምዕራፍ ነብዩን ሙሐመድ (ﷺ) ... በማለት ይቅር እንዲሉ እንዳዘዛቸው ሁሉ በዚህኛውም ምዕራፍም ነብዩ ሙሳ (ﷺ) .... ማለታቸውን ያወሳል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

## በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

حمٓ ١

**1.** ሓ፤ ሚይም፤✱

✱ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፣ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

وَٱلۡكِتَٰبِ ٱلۡمُبِينِ ٢ إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ فِي لَيۡلَةٖ مُّبَٰرَكَةٍۚ إِنَّا كُنَّا مُنذِرِينَ ٣ فِيهَا يُفۡرَقُ كُلُّ أَمۡرٍ حَكِيمٍ ٤ أَمۡرٗا مِّنۡ عِندِنَآۚ إِنَّا كُنَّا مُرۡسِلِينَ ٥ رَحۡمَةٗ مِّن رَّبِّكَۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلسَّمِيعُ ٱلۡعَلِيمُ ٦ رَبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَآۖ إِن كُنتُم مُّوقِنِينَ ٧ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۖ رَبُّكُمۡ وَرَبُّ ءَابَآئِكُمُ ٱلۡأَوَّلِينَ ٨

**2-8.** ሁሉን ነገር አብራሪ በሆነው መጽሐፍ እምላለሁ። እኛ ቁርኣኑን በዚያች በተባረከችው ሌሊት✱[1] ውስጥ አወረድነው። እኛ አስፈራሪዎች ነበርንና። በውስጧ የተወሰነው ነገር ሁሉ ይለያል። ከእኛ ዘንድ የሆነ ትዕዛዝ ሲሆን አወረድነው። እኛ መልዕክተኞችን ላኪዎች ነበርንና። (መልዕክተኞች) ከጌታ በሆነው ችሮታ ተላኩ። እነሆ እርሱ ሰሚና አዋቂ ነውና። የሰማያት፤ የምድር እና በመካከላቸው ያሉ ነገሮች ሁሉ ጌታ ከሆነው (ተላኩ)፤ የምታረጋግጡ እንደሆናችሁ (ነገሩ እንዳልነው መሆኑን እወቁ)። ከእርሱም ሌላ አምላክ የለም፤ ህያው ያደርጋል፤ ህይወትም ይነሳል✱[2]፤ ጌታችሁ የመጀመሪያዎቹ አባቶቻችሁም ጌታ ነው።

✱1 ያን ታላቅና የተባረከ ቁርኣን በዚያች ታላቅና የተባረከች ሌሊት በዚያ በተባረከው ሀገር በመካ በዚያ በተባረከው ታላቅ ሰው ላይ ያወረደበት ሌሊት ማለት ነው።

✱2 በጠዋት ስትነሳ አልሀምዱሊላሂ አል-ለዚ አህያኒ በዕደ ማ አማተኒ ወኢለይሂ አን-ኑሹር የሚለውን አንብብ፤ ከዚያም የዱዓውን መልዕክት ለማጣጣም ስትሞክር የዚህን ታላቅ ስም መልእክት ትረዳለህ።

### ከጭስ (1-8) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
2. የቂያማን ቀን ምልክቶች በጥቂቱም ቢሆን ማስታወስ፤
3. ስሜትን ማስታገስ መጠንቀቅ፤
4. ስሜቱን የሚከተል ሁሉ ለዲኑ ጥቅም እንደሌለው፤
5. የለይለተል ቀድርን ትልቅነት፤
6. በዚያ ሌሊት ቁርኣን መውረዱ በየ አመቱ ሪዝቅ መከፋፈሉ ጥቂቶቹ መሆናቸውን ነው፤

بَلۡ هُمۡ فِي شَكّٖ يَلۡعَبُونَ ٩ فَٱرۡتَقِبۡ يَوۡمَ تَأۡتِي ٱلسَّمَآءُ بِدُخَانٖ مُّبِينٖ ١٠
يَغۡشَى ٱلنَّاسَۖ هَٰذَا عَذَابٌ أَلِيمٞ ١١ رَّبَّنَا ٱكۡشِفۡ عَنَّا ٱلۡعَذَابَ إِنَّا مُؤۡمِنُونَ ١٢

**9-12.** በእውነት እነርሱ የሚጫወቱ ሲሆኑ በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፣ ሰዎችን የሚሸፍን በሆነ ግልፅ ጭስ ሰማይ የምትመጣበትን ቀን ተጠባበቅ። ይህ አሳማሚ ቅጣት ነው። ጌታችን ሆይ፣ በእኛ ላይ ቅጣትን ግለጥልን✳። እኛ አማኞች ነንና (ይላሉ።)

✳ ውድ ወንድሜ ይህንን አንቀጽ ስታነብ ለአንድ አፍታም ቢሆን በዓለም ላይ ለተቸገሩ ሁሉ እንዲደርስላቸው አላህን ጠይቅላቸው።

ከጭስ ምዕራፍ (10-12) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የዚህ አንቀፅ መልዕክት በተመለከተ የተፍሲር ምሁራን ዘንድ የተለያዩ አመለካከቶች አሉ አንደኛው ቁረይሾች ኢስላምን አልቀበልም ባሉ ጊዜ ነብዩ ሙሐመድ ዱዓ አደረጉባቸው አጥንት እስኪሚበሉ ደርሰው በረሀቡ የተነሳ ወደ ሰማይ ሲመለከቱ ጭስና ጭጋግ መስሏቸው ነበር። ከዚያም ወደ ነብዩ ሙሐመድ ሰዎች በመላክ በኒ ሙዶሮች አለቁ ዝናብ ለምኑላቸው ሲሏቸው ዱዓ አደረጉላቸው። ዝናብ ዘነበ ችግሩ ተወገደ በዚህ አባባል ጭስ የተባለው ነገር ተከስቶ ያለፈ ነገር ነው ማለት ነው።

ሁለተኛው ደግሞ ከቂያማ ቀን ግዙፍ ምልቶች መካከል ግዙፍ አስር ምልክቶች መካከል አንዱ ነው በሚል የሆነው ጭስ ነው በሚል የተረዱ ሲኖሩ በዚህ አባባል ደግሞ ምልክቱ ገና ወደ ፊት የሚመጣ እንጂ ያለፈ አይደለም ይላሉ። ከቂያማ ምልክቶች መካከል አንዱ እንደሆነ በሐዲስ ቢነገርም ነብዩ እንዲጠባበቁት የታዘዙት ጭስ ግን በዚያው በዘመናቸው የተከሰተው ነው ይላሉ።

أَنَّىٰ لَهُمُ ٱلذِّكۡرَىٰ وَقَدۡ جَآءَهُمۡ رَسُولٞ مُّبِينٞ ١٣ ثُمَّ تَوَلَّوۡاْ عَنۡهُ
وَقَالُواْ مُعَلَّمٞ مَّجۡنُونٌ ١٤ إِنَّا كَاشِفُواْ ٱلۡعَذَابِ قَلِيلًاۚ إِنَّكُمۡ عَآئِدُونَ ١٥
يَوۡمَ نَبۡطِشُ ٱلۡبَطۡشَةَ ٱلۡكُبۡرَىٰٓ إِنَّا مُنتَقِمُونَ ١٦

**13-16.** (ቅጣት በወረደ ጊዜ) ለእነርሱ መገሰፅ እንዴት ይኖራቸዋል አስረጅ መልዕክተኛ የመጣላቸው እና በአላህ የካዱ ሲሆኑ፣ ከዚያ ከእርሱ የዞሩ ከሰው የተስተማረ እብድ ነው ያሉም ሲሆኑ እኛ ቅጣትን ለጥቂት ጊዜ ገላጮች ነን፤ እናንተ ግን ወደ ክህደታችሁ በእርግጥ አንደገና ተመላሾች ናችሁ✳ ታላቂቱን ብርቱ አያያዝ በምንይዝበት ቀን እኛ ተበቃዮች ነን።

✳ የሚመክርህን ሰው ተቀበለው፤ አላህ ግዜ ቢሰጥም ጭራሽ የማይተው መሆኑን አስተውሉ፤

ከጭስ ምዕራፍ ከ (15-16) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ኢብኑ ዐባስ ይህ ቀን የቂያማ ቀን ማለት ነው ሲሉ ኢብኑ መስዑድ ደግሞ የበድር ዕለት የተከሰተውን ሽንፈት ለመግለፅ ነው ይላሉ። (ሱዩጢ)

۞ وَلَقَدۡ فَتَنَّا قَبۡلَهُمۡ قَوۡمَ فِرۡعَوۡنَ وَجَآءَهُمۡ رَسُولٞ كَرِيمٌ ﴿١٧﴾ أَنۡ أَدُّوٓاْ إِلَيَّ عِبَادَ ٱللَّهِۖ إِنِّي
لَكُمۡ رَسُولٌ أَمِينٞ ﴿١٨﴾ وَأَن لَّا تَعۡلُواْ عَلَى ٱللَّهِۖ إِنِّيٓ ءَاتِيكُم بِسُلۡطَٰنٖ مُّبِينٖ ﴿١٩﴾ وَإِنِّي عُذۡتُ
بِرَبِّي وَرَبِّكُمۡ أَن تَرۡجُمُونِ ﴿٢٠﴾ وَإِن لَّمۡ تُؤۡمِنُواْ لِي فَٱعۡتَزِلُونِ ﴿٢١﴾ فَدَعَا رَبَّهُۥٓ أَنَّ هَٰٓؤُلَآءِ قَوۡمٞ
مُّجۡرِمُونَ ﴿٢٢﴾ فَأَسۡرِ بِعِبَادِي لَيۡلًا إِنَّكُم مُّتَّبَعُونَ ﴿٢٣﴾ وَٱتۡرُكِ ٱلۡبَحۡرَ رَهۡوًاۖ إِنَّهُمۡ جُندٞ مُّغۡرَقُونَ ﴿٢٤﴾
كَمۡ تَرَكُواْ مِن جَنَّٰتٖ وَعُيُونٖ ﴿٢٥﴾ وَزُرُوعٖ وَمَقَامٖ كَرِيمٖ ﴿٢٦﴾ وَنَعۡمَةٖ كَانُواْ فِيهَا فَٰكِهِينَ ﴿٢٧﴾
كَذَٰلِكَۖ وَأَوۡرَثۡنَٰهَا قَوۡمًا ءَاخَرِينَ ﴿٢٨﴾ فَمَا بَكَتۡ عَلَيۡهِمُ ٱلسَّمَآءُ وَٱلۡأَرۡضُ وَمَا كَانُواْ مُنظَرِينَ ﴿٢٩﴾

**17-29.** ከእነርሱ በፊት የፈርዖንን ህዝቦች በእርግጥ ሞከርን። ክቡር መልዕክተኛም አመጣንላቸው። የአላህን ባሮች ወደ እኔ አድርሱ (ለኔ ስጡኝ)። እኔ ለእናንተ ታማኝ መልዕክተኛ ነኝና። በአላህም ላይ አትኩሩ እኔ ግልፅ የሆነን አስረጅ ያመጣሁላችሁ ነኝና (በማለት መጣላቸው) እኔ እንዳትወግሩኝ በጌታዬና በጌታችሁ ተጠብቂያለሁ። በእኔም ባታምኑ ራቁኝ ተውኝ አለ። ቀጥሎም (ስለዛቱበት) እነዚህ አመፀኞች ህዝቦች ናቸው፤ አጥፉቸው ሲል ጌታውን ለመነ። ጌታውም ባሮቼን ይዘህ በሌሊት ሂድ፤ እናንተ የሚከተሉዋችሁ ናችሁና። ባህሩንም የተከፈተ ሆኖ ተወው፤ እነርሱ የሚሰምጡ ሰራዊት ናቸውና አለው። ከአትክልቶችና ከምንጮች ብዙ ነገሮችን ተው። ከአዝመራዎችም ከመልካም መቀመጫም በእርሷ ተደሳቾች ከነበሩባትም ድሎት ብዙን ነገር ተው። ነገሩ እንደዚህ ሆነ፤ ሌሎችንም ህዝቦች አወረስናት። ሰማይና ምድር በእነርሱ ላይ አላለቀሱም። የሚቆዩም አልነበሩም።

وَلَقَدۡ نَجَّيۡنَا بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ مِنَ ٱلۡعَذَابِ ٱلۡمُهِينِ ﴿٣٠﴾ مِن فِرۡعَوۡنَۚ إِنَّهُۥ كَانَ عَالِيٗا مِّنَ
ٱلۡمُسۡرِفِينَ ﴿٣١﴾ وَلَقَدِ ٱخۡتَرۡنَٰهُمۡ عَلَىٰ عِلۡمٍ عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿٣٢﴾ وَءَاتَيۡنَٰهُم مِّنَ ٱلۡأٓيَٰتِ مَا فِيهِ
بَلَٰٓؤٞاْ مُّبِينٌ ﴿٣٣﴾ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَيَقُولُونَ ﴿٣٤﴾ إِنۡ هِيَ إِلَّا مَوۡتَتُنَا ٱلۡأُولَىٰ وَمَا نَحۡنُ بِمُنشَرِينَ ﴿٣٥﴾
فَأۡتُواْ بِـَٔابَآئِنَآ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٣٦﴾

**30-36.** የኢስራኤል ልጆችን ከዚያ አዋራጅ ከሆነ ከፈርዖን ስቃይ በእርግጥ አዳንናቸው። እርሱ የኮራ ከወሰን አላፊዎች አንዱ ነበርና። ከማወቅም ጋር በዘመናቸው ከነበሩት መካከል በእርግጥ መረጥናቸው። በተአምራቶችም በውስጡ ግልፅ የሆነ ፈተና ያለበትን ሰጠናቸው። እነዚህ የመካ ካሓዲያን በእርግጥ ይላሉ፡- እርሷ የፊተኛይቱ ሞታችን እንጅ አይደለችም እኛም የምንቀሰቀስ አይደለንም። እውነተኞችም እንደሆናችሁ አባቶቻችንን አምጡልን።

أَهُمْ خَيْرٌ أَمْ قَوْمُ تُبَّعٍ وَٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ أَهْلَكْنَـٰهُمْ ۖ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ مُجْرِمِينَ ﴿٣٧﴾

37. እነርሱ በላጮች ናቸውን? ወይም የቱበዕ ህዝቦችና እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩትን አጠፋናቸው እነርሱ አመፀኞች ነበሩ።

وَمَا خَلَقْنَا ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا لَـٰعِبِينَ ﴿٣٨﴾ مَا خَلَقْنَـٰهُمَآ إِلَّا بِٱلْحَقِّ وَلَـٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٣٩﴾ إِنَّ يَوْمَ ٱلْفَصْلِ مِيقَـٰتُهُمْ أَجْمَعِينَ ﴿٤٠﴾ يَوْمَ لَا يُغْنِى مَوْلًى عَن مَّوْلًى شَيْـًٔا وَلَا هُمْ يُنصَرُونَ ﴿٤١﴾ إِلَّا مَن رَّحِمَ ٱللَّهُ ۚ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٤٢﴾

38-42. ሰማያትን ምድርን እና በሁለቱ መካከል ያለውንም ሁሉ ቀላጆች ሆነን አልፈጠርንም። ሁለቱንም በምር እንጂ አልፈጠርናቸውም። ግን አብዛሀኞቻቸው አያውቀውም። የመለያው ቀን ለሁሉም ቀጠሯቸው ነው። ዘመድ ከዘመዱ ምንንም የማይጠቅምበት እነርሱም የማይረዱበት ቀን ነው። አላህ ያዘነለት ሰውና ያመነ ብቻ ሲቀር። (እርሱ ይረዳል) እርሱ አሸናፊና አዛኙ ነውና።

إِنَّ شَجَرَتَ ٱلزَّقُّومِ ﴿٤٣﴾ طَعَامُ ٱلْأَثِيمِ ﴿٤٤﴾ كَٱلْمُهْلِ يَغْلِى فِى ٱلْبُطُونِ ﴿٤٥﴾ كَغَلْىِ ٱلْحَمِيمِ ﴿٤٦﴾

43-46. የዘቁም ዛፍ የኃጢአተኞች ምግብ ናት። ልክ እንደ ዘይት አተላ ነው። በሆዶች ውስጥ። እንደገነፈለ ውሃ አፈላል የሚፈላ ነው።

ከጭስ ምዕራፍ (43) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡ ጀህል ተምርና አይቤ አምጥቶ ይህን በዚህ እናወርዳለን ካለ በኋላ ይህ እኮ ነው ሙሐመድ የሚቀጥራችሁ እያለ በማፌዙ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

خُذُوهُ فَٱعْتِلُوهُ إِلَىٰ سَوَآءِ ٱلْجَحِيمِ ﴿٤٧﴾ ثُمَّ صُبُّوا۟ فَوْقَ رَأْسِهِۦ مِنْ عَذَابِ ٱلْحَمِيمِ ﴿٤٨﴾ ذُقْ إِنَّكَ أَنتَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْكَرِيمُ ﴿٤٩﴾ إِنَّ هَـٰذَا مَا كُنتُم بِهِۦ تَمْتَرُونَ ﴿٥٠﴾ إِنَّ ٱلْمُتَّقِينَ فِى مَقَامٍ أَمِينٍ ﴿٥١﴾ فِى جَنَّـٰتٍ وَعُيُونٍ ﴿٥٢﴾ يَلْبَسُونَ مِن سُندُسٍ وَإِسْتَبْرَقٍ مُّتَقَـٰبِلِينَ ﴿٥٣﴾ كَذَٰلِكَ وَزَوَّجْنَـٰهُم بِحُورٍ عِينٍ ﴿٥٤﴾ يَدْعُونَ فِيهَا بِكُلِّ فَـٰكِهَةٍ ءَامِنِينَ ﴿٥٥﴾ لَا يَذُوقُونَ فِيهَا ٱلْمَوْتَ إِلَّا ٱلْمَوْتَةَ ٱلْأُولَىٰ ۖ وَوَقَىٰهُمْ عَذَابَ ٱلْجَحِيمِ ﴿٥٦﴾ فَضْلًا مِّن رَّبِّكَ ۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴿٥٧﴾

**47-57.** ያዙትና ወደገሀነም መካከል (ውስጥ) በሀይል ጎትቱት (ገፍትሩት)። ከዚያ በራሱ ላይ ከፈላ ውሃ ስቃይ አንቧቡበት። ቅመስ አንተ አሸናፊ፣ ክቡር እና ትልቅ የነበርክ ነህና (ይባላል)። ይህ ያ በእርሱ ትጠራጠሩበት የነበራችሁት ነው (ይባላሉ)። ጥንቁቆች በእርግጥ በፀጥተኛ መኖሪያ ውስጥ ናቸው። በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው። ፊት ለፊት የተቅጣጩ ሆነው ከስስ ሐርና ከወፍራም ሐር ይለብሳሉ። ነገሩ እንደዚህ ነው ዓይናማዎች የሆኑን ሴቶችም እናጠናዳቸዋለን። በእርሷ ውስጥም የተማመኑ ሆነው ከፍራፍሬ ሁሉ ያዛሉ። የፊተኛይቱን ሞት እንጂ ዳግመኛ በእርሷ ውስጥ ሞትን አይቀምሱም✳፤ የገሀነምንም ቅጣት ከጌታህ በሆነ ትርፋት ጠበቃቸው። ታላቅ እድል ማለት ይህ ነው።

✳ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ.... «ሞት በሞከተ በግ ተመስሎ በጀነትና በእሳት መካከል ይመጣና ይታረዳል ከዛም የጀነት ሰዎች ሆይ! ሁልግዜም በዚህ ጀነትውስጥ ዘውታሪዎች ናችሁ፤ የእሳት ሰዎች ሆይ! ከዚህ በሁዋላ ከእሳት መውጣት የለም፤ ሞትም የለም» ይባላሉ ብለዋል። ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ ለጀነት ሰዎች «ከዚህ በኋላ አንድም ቀን የማትታመሙበት ሙሉ ጤና አላችሁ፤ ሞት የሚባል የማያቋርጠው ሂዎት አለላችሁ፤ መቼም ቢሆን የማይቋረጥ ደስታ ለናንተ ነው፤ አንድ ቀን እርጅና የማያቋርጠው ወጣትነት ለናንተ ተወስኖላችኋል» ይባላሉ ብለዋል።

ከጭስ (49) ኛውአንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡ ጀህልን በመንገድ ላይ አግኝተውት አላህ ወየውልህ! ወየውልህ! እንድልህ አዞኛል በማለታቸው በጣም ተቆጥቶ እኔ እኮ የተከበርኩ የመካን ህዝብ በሙሉ መምራት የምችል ሰው ነኝ በምንድን ነው የምትዝትብኝ፤ በማለቱ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ ናሱዩጢ)

فَإِنَّمَا يَسَّرۡنَٰهُ بِلِسَانِكَ لَعَلَّهُمۡ يَتَذَكَّرُونَ ﴿٥٨﴾ فَٱرۡتَقِبۡ إِنَّهُم مُّرۡتَقِبُونَ ﴿٥٩﴾

**58-59.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቁርኣኑንም በቋንቋህ ያገራነው ህዝቦችህ ይገነዘቡት ዘንድ ብቻ ነው። ተጠባበቅ። እነርሱም ተጠባባቂዎች ናቸው።

**ከጭስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (9-59) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) ማፅናናት፤
2. ቁረይሽን ማስጠንቀቅ፤
3. የኑህን ዘመን ማእበል ማስታወስ፤
4. አላህ ለዚህ ኡማህ ቁርአንን ማግራቱን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የጭስ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (45)
# የተንበርካኪዋ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ጃሲያ)

سُورَةُ الجَاثِيَةِ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (37) ናቸው።**

**የሱረቱ አል-ጃሲያ መግቢያ**

ቁርኣን ከአላህ የወረደ መሆኑን ገልፆ ስለ ትክክለኛው እምነት ብዙ ማስረጃዎችን ደርድሮ በከሀዲዎች ላይም እርግማን ያስከትላል። ከዚያ አላህ ለሰዎች የዋለውን ፀጋ በመዘርዘር አማኞች በካሀዲያን ጥፋት እንዲያልፍ ይመክራል። በመቀጠልም አላህ ለበኒ ኢስራኢሎች የዋለላቸውን ውለታና በመካከላቸው ለተፈጠረው መለያየት የቂያማ ቀን ውሳኔ እንደሚሰጥ ገልፆ እውነትን የተከለተሉና ስሜታቸውን በመከተል ሙቶ መነሳትን ያስተባበሉና ለማይችሉ ቅድመ አያቶቻችንን ህያው ያድርግ በማለት የተከራከሩትን በመለያየት ያብራራና የቂያማ ዕለት ሁሉ የየራሱ መዝገብ እንደሚሰጠው አውስቶ አላህን በማሞገስ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

حمٓ ﴿١﴾ تَنزِيلُ ٱلۡكِتَٰبِ مِنَ ٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَكِيمِ ﴿٢﴾

**1-2.** ሓ፣ ሚይም፣* የመጽሐፉ መወረድ አሸናፊ፤ ጥበበኛ ከሆነው ከአላህ ነው።

✷ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ፲ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

إِنَّ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ لَأٓيَٰتٖ لِّلۡمُؤۡمِنِينَ ﴿٣﴾ وَفِي خَلۡقِكُمۡ وَمَا يَبُثُّ مِن دَآبَّةٍ ءَايَٰتٞ
لِّقَوۡمٖ يُوقِنُونَ ﴿٤﴾ وَٱخۡتِلَٰفِ ٱلَّيۡلِ وَٱلنَّهَارِ وَمَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ مِن رِّزۡقٖ فَأَحۡيَا بِهِ
ٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ مَوۡتِهَا وَتَصۡرِيفِ ٱلرِّيَٰحِ ءَايَٰتٞ لِّقَوۡمٖ يَعۡقِلُونَ ﴿٥﴾ تِلۡكَ ءَايَٰتُ ٱللَّهِ نَتۡلُوهَا
عَلَيۡكَ بِٱلۡحَقِّۖ فَبِأَيِّ حَدِيثِۭ بَعۡدَ ٱللَّهِ وَءَايَٰتِهِۦ يُؤۡمِنُونَ ﴿٦﴾

**3-6.** በሰማያትና በምድር ውስጥ ለምዕመናን ሁሉ ለችሮታው አያሌ እርግጠኛ ምልክቶች አሉ። (ሰዎች ሆይ!) እናንተንም በመፍጠርና ከተንቀሳቃሽ ነገሮች (በምድር ላይ) የሚበተነውን ሁሉ (በመፍጠሩ) ለሚያረጋግጡ ህዝቦች ብዙ ተአምራቶች አሉ። በሌሊትና በቀን መተካካትም አላህ ከሰማይ ባወረደው

ዝናብ በእርሱም ምድርን ከሞተች በኋላ ህያው በማድረጉ፤ ነፍሶችንም (በየአቅጣጫው) በማዘዋወሩ ለሚያውቁ ህዝቦች ሁሉ በቂ ማስረጃዎች አሉ። እነዚያ ከአንተ በላይ በእውነት የምናነባቸው ሲሆኑ የአላህ ማስረጃዎች አሉ። ከአላህና ከማስረጃዎችም ወዲያ በየትኛው ንግግር ያምናሉ?

وَيْلٌ لِّكُلِّ أَفَّاكٍ أَثِيمٍ ۝٧ يَسْمَعُ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ تُتْلَىٰ عَلَيْهِ ثُمَّ يُصِرُّ مُسْتَكْبِرًا كَأَن لَّمْ يَسْمَعْهَا ۖ فَبَشِّرْهُ بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ۝٨

**7-8.** ውሸታሞች ኃጢአተኛ ለሆነ ሰው ሁሉ ወዩውለት (ጥፋት ተገባው)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የአላህን አንቀፆች በእርሱ ላይ የሚነበቡለት ሲሆኑ ይሰማል ከዚያ የኮራ ሲሆን እንዳልሰማ ሆኖ በክህደቱ ላይ ይዘወትራል በአሳማሚ ቅጣት አብስረው።

وَإِذَا عَلِمَ مِنْ ءَايَٰتِنَا شَيْـًٔا ٱتَّخَذَهَا هُزُوًا ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ لَهُمْ عَذَابٌ مُّهِينٌ ۝٩

**9.** ከአንቀፆቻችንም አንዲትን ነገር ባወቀ ጊዜ መሳለቂያ አድርጎ ይይዛታል። እነዚያ ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አለላቸው።

مِّن وَرَآئِهِمْ جَهَنَّمُ ۖ وَلَا يُغْنِى عَنْهُم مَّا كَسَبُوا۟ شَيْـًٔا وَلَا مَا ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَوْلِيَآءَ ۖ وَلَهُمْ عَذَابٌ عَظِيمٌ ۝١٠

**10.** ከፊታቸውም ገሀነም አለች የሰበሰቡት ሀብት ከእነርሱ ላይ ምንንም አይመልስላቸውም ከአላህ ሌላም ረዳቶች አድርገው የያዙዋቸው ሁሉ ምንንም አይጠቅሟቸውም። ለእነርሱም ታላቅ ቅጣት አለላቸው።

هَٰذَا هُدًى ۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ بِـَٔايَٰتِ رَبِّهِمْ لَهُمْ عَذَابٌ مِّن رِّجْزٍ أَلِيمٌ ۝١١

**11.** ይህ ቁርኣን መሪ ነው። እነዚያ በጌታቸው አንቀፆች የካዱት ሰዎች ሁሉ ለእነርሱ ከብርቱ ቅጣት ድርሻቸው አለላቸው።

۞ ٱللَّهُ ٱلَّذِى سَخَّرَ لَكُمُ ٱلْبَحْرَ لِتَجْرِىَ ٱلْفُلْكُ فِيهِ بِأَمْرِهِۦ وَلِتَبْتَغُوا۟ مِن فَضْلِهِۦ وَلَعَلَّكُمْ تَشْكُرُونَ ۝١٢ وَسَخَّرَ لَكُم مَّا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ جَمِيعًا مِّنْهُ ۚ إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَءَايَٰتٍ لِّقَوْمٍ يَتَفَكَّرُونَ ۝١٣

**12-13.** አላህ ባህርን በውስጡ ታንኳዎች በፈቃዱ እንዲንሻለሉበት ከችሮታውም እንድትፈልጉበት እንድታመሰግኑትም ለእናንተ የገራላችሁ ነው። ለእናንተ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ በመላ ከእርሱ ሲሆን የገራላችሁ ነው። በዚህ ለሚያስተነትኑ ህዝቦች አያሌ ተዐምራት አለበት።

قُل لِّلَّذِينَ ءَامَنُواْ يَغۡفِرُواْ لِلَّذِينَ لَا يَرۡجُونَ أَيَّامَ ٱللَّهِ لِيَجۡزِيَ قَوۡمَۢا بِمَا كَانُواْ يَكۡسِبُونَ ﴿١٤﴾

**14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለእነዚያ ለአመኑት ሰዎች ምህረት አድርጉ በላቸው። ለእነዚያ የአላህን ቀናት ለማይፈሩት ይምራሉና ህዝቦችን ይሰሩት የነበሩትን ነገር ይመነዳ ዘንድ ምህረት አድርጉ በላቸው።

ከተንበርካኪዋ (14) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክኒያት:. ዐውፍ ቢን ማሊክ ከነብዩ (ﷺ) ጋር ወደ አይሁዶች መሰብሰቢያ ሂደን ነብዩ እስቲ ከመሐከላችሁ (12) ሰዎችን በአላህ አንድነትና ነብዩ (ﷺ) ነብይነት የሚመሰክሩ ሰዎች አሳየኝ አላህ አይሁድ ከተባለ ሁሉ ቁጣውን ያነሳልና ሲሏቸው አንድም መልስ ሳይሰጣቸው ከየት እንደመጣ ያልታወቀ ሰው ሙሐመድ እንዳልከው ነው አለና ወደ አይሁዶች ዞወር ብሎ እኔ በእናንተ ዘንድ ማንነቴን ታውቃላቹሁ ሲላቸው አዎ ከአንተ እና ከአባትህ የተሻለ ስለ አላህ መፅሐፍ የሚያውቅ በመሀላችን እንደሌለ ነው የምናውቀው በማለት መለሱለት እሱም እንግዲያው ይህ ሰው በተውራት የተነገረለት ነብይ መሆኑን እመሰክራለሁ ሲላቸው ወዲያውኑ አስተባብለው መጥፎ መጥፎ ቃል መናገራቸውን ምክንያት አድርጎ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ይህ ሰው አብደላህ ቢን ሰላም ነበሩ። (ሱዩጢ)

(ሀ) ካፊሮች እኛ እኛ እያሉ ራሳቸውን ይክቡ ስለነበሩና እኛ የተሻለ ነገር ቢሆን ኖሮ ማንም እኛን ባልቀደመን ነበር በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

(ለ) አንዲት ዚኒራ የተባለች የዑመር ቢን -አል-ኸጣብ ባሪያ ነበረች ከዑመር በፊት ሰልማ ስለነበር ዑመር እስከሚታክታቸው ድረስ ይገርፏት ነበር ካፊሮች ሙሐመድ ያመጣው ነገር ጥሩ ነገር ቢሆን ኑሮ ዘኒራ ባልቀደመችን ነበር በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

(ሐ) ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ሂጅራ ከማድረጋቸው በፊት አንድ ጣኦት አምላኪ ሰድቧቸው ሊረግጡት አስበው ሳለ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው የሚሉም አለ።

مَنۡ عَمِلَ صَٰلِحٗا فَلِنَفۡسِهِۦۖ وَمَنۡ أَسَآءَ فَعَلَيۡهَاۖ ثُمَّ إِلَىٰ رَبِّكُمۡ تُرۡجَعُونَ ﴿١٥﴾

**15.** (ሰዎች ሆይ!) መልካምን የሰራ ሰው ሁሉ ጥቅሙ ለነፍሱ ነው። ክፉንም ተግባር የሰራ ሰው ሁሉ ክፋቱ በእርሱው ላይ ነው። ከዚያ ሁላችሁም ወደ ጌታችሁ ትመለሳላችሁ።

وَلَقَدۡ ءَاتَيۡنَا بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحُكۡمَ وَٱلنُّبُوَّةَ وَرَزَقۡنَٰهُم مِّنَ ٱلطَّيِّبَٰتِ وَفَضَّلۡنَٰهُمۡ
عَلَى ٱلۡعَٰلَمِينَ ﴿١٦﴾ وَءَاتَيۡنَٰهُم بَيِّنَٰتٖ مِّنَ ٱلۡأَمۡرِۖ فَمَا ٱخۡتَلَفُوٓاْ إِلَّا مِنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَهُمُ ٱلۡعِلۡمُ
بَغۡيَۢا بَيۡنَهُمۡۚ إِنَّ رَبَّكَ يَقۡضِي بَيۡنَهُمۡ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ فِيمَا كَانُواْ فِيهِ يَخۡتَلِفُونَ ﴿١٧﴾

**16-17.** ለኢስራኤል ልጆችም መጽሐፍን፤ ሕግን እና ነብይነትን በእርግጥ ሰጠናቸው። ከመልካም ሲሳዩችም ለገስንላቸው። በዘመናቸው ከነበሩት የዓለማት ህዝብ ላይም አበለጥናቸው። ከትዕዛዝም ግልፅ ነገሮችን ሰጠናቸው። እውቀቱም ከመጣላቸው በኋላ በመካከላቸው ለምቀኝነት እንጅ ለሌላ አልተለያዩም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ በትንሳኤ ቀን በዚያ እነርሱ ይለያዩበት በነበሩት ነገር በመካከላቸው በትክክል ይፈርዳል።

ثُمَّ جَعَلْنَٰكَ عَلَىٰ شَرِيعَةٍ مِّنَ ٱلْأَمْرِ فَٱتَّبِعْهَا وَلَا تَتَّبِعْ أَهْوَآءَ ٱلَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ ﴿١٨﴾ إِنَّهُمْ
لَن يُغْنُوا۟ عَنكَ مِنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔا ۚ وَإِنَّ ٱلظَّٰلِمِينَ بَعْضُهُمْ أَوْلِيَآءُ بَعْضٍ ۖ وَٱللَّهُ وَلِىُّ ٱلْمُتَّقِينَ ﴿١٩﴾

**18-19.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዚያ ከሃይማኖቱ በትክክለኛው ሕግ ላይ አደረግንህ። ስለዚህ ተከተለው። የነዚያን የማያውቁትን ህዝቦች ዝንባሌዎች አትከተል። እነርሱ ከአላህ ቅጣት ምንንም ከአንተ አይገፈትሩልህምና በደለኞችም ከፊላቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው። አላህ የጥንቁቆቹ ወዳጅ ነውና።

هَٰذَا بَصَٰٓئِرُ لِلنَّاسِ وَهُدًى وَرَحْمَةٌ لِّقَوْمٍ يُوقِنُونَ ﴿٢٠﴾ أَمْ حَسِبَ ٱلَّذِينَ ٱجْتَرَحُوا۟ ٱلسَّيِّـَٔاتِ أَن
نَّجْعَلَهُمْ كَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ سَوَآءً مَّحْيَاهُمْ وَمَمَاتُهُمْ ۚ سَآءَ مَا يَحْكُمُونَ ﴿٢١﴾

**20-21.** ይህ ቁርኣን ለሰዎች የልብ ብርሃን ነው። ለሚያረጋግጡትም ህዝቦች ሁሉ መሪና እዝነት ነው። እነዚያ ኃጢአቶችን እየሰሩ ሕይወታቸውም ሞታቸውም ትክክል ሲሆን እንደነዚያ እንዳመኑት መልካሞችን እንደሰሩ ልናደርጋቸው ያስባሉን? (አይሰቡ)። (ይህ ከሆነ) የሚፈርዱት ፍርዱ ምንኛ ከፋ፣

وَخَلَقَ ٱللَّهُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ بِٱلْحَقِّ وَلِتُجْزَىٰ كُلُّ نَفْسٍۭ بِمَا كَسَبَتْ وَهُمْ لَا يُظْلَمُونَ ﴿٢٢﴾

**22.** አላህ ሰማያትና ምድርን ለችሮታው እንዲያመለክቱባቸውና ነፍስም ሁሉ በሰራችው ስራ ትመነዳ ዘንድ በትክክል ፈጠረ። እነርሱ አይበደሉም።

أَفَرَءَيْتَ مَنِ ٱتَّخَذَ إِلَٰهَهُۥ هَوَىٰهُ وَأَضَلَّهُ ٱللَّهُ عَلَىٰ عِلْمٍ وَخَتَمَ عَلَىٰ سَمْعِهِۦ وَقَلْبِهِۦ وَجَعَلَ
عَلَىٰ بَصَرِهِۦ غِشَٰوَةً فَمَن يَهْدِيهِ مِنۢ بَعْدِ ٱللَّهِ ۚ أَفَلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٢٣﴾ وَقَالُوا۟ مَا هِىَ إِلَّا حَيَاتُنَا
ٱلدُّنْيَا نَمُوتُ وَنَحْيَا وَمَا يُهْلِكُنَآ إِلَّا ٱلدَّهْرُ ۚ وَمَا لَهُم بِذَٰلِكَ مِنْ عِلْمٍ ۖ إِنْ هُمْ إِلَّا يَظُنُّونَ ﴿٢٤﴾

**23-24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ዝንባሌውን አምላኩ አድርጎ የያዘውን አላህም ከእውቀት ጋር ያጠመመውን በጆሮውና በልቡ ላይም ያተመበትን በዓይኑም ላይ ሺፋን ያደረገበትን ሰው አየህን? ታዲያ ከአላህ ኋላ የሚያቀናው ማነው? አትገሰፁምን? (ከሓዲያን እርሷም ሕይወት) የቅርቢቱ ሕይወታችን ብቻ እንጂ ሌላ አይደለችም። እንሞታለን። ህያውም እንሆናለን።* ከጊዜም (ማለፍ) በስተቀር ሌላ አያጠፋንም አሉ። ለእነርሱም በዚህ በሚሉት ምንም እውቀት የላቸውም። እነርሱ የሚጠራጠሩ እንጂ ሌላ አይደሉም።

* የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «አላህ እንዲህ ብሏል «የሰው ልጅ ዘመንን ይዘልፋል ነገር ግን እኔ ዘመን ነኝ። ሁሉም ነገሮች በእጆቼ ናቸው። የቀንና የሌሊት መፈራረቅንም አድርጋለሁ» «እኔ ዘመን ነኝ» ማለት «ከእኔ ዘመንን ፈጣሪ ነኝ። የፍጥረታትንም ጉዳዩች እቆጣጠራለሁ። ማንም ሰው ለዘመን መልካምም ሆነ መጥፎ ባህሪ ሊሰጠው ፈፅሞ አይችልም። ሁሉም ነገር በአላህ እጅ ነው ስለዚህ ሁሉንም ነገር ሊቀያየር የሚችለው እሱ ብቻ ነው» ማለት ነው።

وَإِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتُنَا بَيِّنَٰتٖ مَّا كَانَ حُجَّتَهُمۡ إِلَّآ أَن قَالُواْ ٱئۡتُواْ بِـَٔابَآئِنَآ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٢٥ قُلِ ٱللَّهُ يُحۡيِيكُمۡ ثُمَّ يُمِيتُكُمۡ ثُمَّ يَجۡمَعُكُمۡ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ لَا رَيۡبَ فِيهِ وَلَٰكِنَّ أَكۡثَرَ ٱلنَّاسِ لَا يَعۡلَمُونَ ٢٦

**25-26.** አንቀፆቻችን ግልፆች ሆነው በእነርሱ ላይ በተነበቡላቸው ጊዜ ክርክራቸው እውነተኞች እንደሆናችሁ እስቲ የቀድሞ አባቶቻችን አምጡ ማለት እንጂ ሌላ አልነበረም። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ህያው ያደርጋችኋል ከዚያ ያሞታችኋል ከዚያ በትንሳኤ ቀን ይሰበስባችኋል። በእነርሱም ጥርጥር የለበትም። ግን አብዛሀኛዎቹ ሰዎች አያውቁም በላቸው።

وَلِلَّهِ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ وَيَوۡمَ تَقُومُ ٱلسَّاعَةُ يَوۡمَئِذٖ يَخۡسَرُ ٱلۡمُبۡطِلُونَ ٢٧

**27.** የሰማያትና የምድር ግዛት የአላህ ብቻ ነው። ሰዓቲቱም በምትከሰትበት ቀን ያን ጊዜ አጥፊዎች ሁሉ ይከስራሉ።

وَتَرَىٰ كُلَّ أُمَّةٖ جَاثِيَةٗۚ كُلُّ أُمَّةٖ تُدۡعَىٰٓ إِلَىٰ كِتَٰبِهَا ٱلۡيَوۡمَ تُجۡزَوۡنَ مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ٢٨ هَٰذَا كِتَٰبُنَا يَنطِقُ عَلَيۡكُم بِٱلۡحَقِّۚ إِنَّا كُنَّا نَسۡتَنسِخُ مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ٢٩

**28-29.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ህዝቦችን ሁሉ ተንበርካኪ ሆነው ታያቸዋለህ። ህዝብ ሁሉ ወደ ግል መጽሐፋቸው ይጠራሉ። ዛሬ ቀደም ሲል ትሰሩት የነበራችሁትን ነገር ትመነዳላችሁ (ይባላሉ)። ይህ መጽሐፋችን ነው። በእናንተ ላይ በእውነት ይናገራል እኛ ያንን ትሰሩ የነበራችሁትን እናስገለብጥ ነበርንና (ይባላሉ)።

فَأَمَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَيُدْخِلُهُمْ رَبُّهُمْ فِى رَحْمَتِهِۦ ۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلْفَوْزُ ٱلْمُبِينُ ﴿٣٠﴾

**30.** እነዚያ በአላህ ያመኑትና መልካሞችን የሰሩት ጌታቸው በእዝነቱ ውስጥ ያስገባቸዋል። ይህ እርሱ ግልፅ የሆነ እድልን ማግኘት ነው።

وَأَمَّا ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓا۟ أَفَلَمْ تَكُنْ ءَايَٰتِى تُتْلَىٰ عَلَيْكُمْ فَٱسْتَكْبَرْتُمْ وَكُنتُمْ قَوْمًا مُّجْرِمِينَ ﴿٣١﴾

**31.** እነዚያም የካዱትማ ለእነርሱ ይባላሉ አንቀፆቼ በእናንተ ላይ ይነበቡ አልነበሩምን? ኮራችሁም ከሓዲዎች ህዝቦች ነበራችሁ።

وَإِذَا قِيلَ إِنَّ وَعْدَ ٱللَّهِ حَقٌّ وَٱلسَّاعَةُ لَا رَيْبَ فِيهَا قُلْتُم مَّا نَدْرِى مَا ٱلسَّاعَةُ إِن نَّظُنُّ
إِلَّا ظَنًّا وَمَا نَحْنُ بِمُسْتَيْقِنِينَ ﴿٣٢﴾

**32.** የአላህ ቀጠሮ እውነት ነው በእርሷ መምጣት (ጥርጥር) የለም በተባለ ጊዜም ሰዓቲቱ ምን እንደሆነች አናውቅም መጠራጠርን የምንጠራጠር እንጂ ሌላ አይደለንም። እኛም አረጋጋጮች አይደለንም አላችሁ።

وَبَدَا لَهُمْ سَيِّـَٔاتُ مَا عَمِلُوا۟ وَحَاقَ بِهِم مَّا كَانُوا۟ بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ﴿٣٣﴾ وَقِيلَ ٱلْيَوْمَ نَنسَىٰكُمْ كَمَا
نَسِيتُمْ لِقَآءَ يَوْمِكُمْ هَٰذَا وَمَأْوَىٰكُمُ ٱلنَّارُ وَمَا لَكُم مِّن نَّٰصِرِينَ ﴿٣٤﴾ ذَٰلِكُم بِأَنَّكُمُ ٱتَّخَذْتُمْ
ءَايَٰتِ ٱللَّهِ هُزُوًا وَغَرَّتْكُمُ ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا ۚ فَٱلْيَوْمَ لَا يُخْرَجُونَ مِنْهَا وَلَا هُمْ يُسْتَعْتَبُونَ ﴿٣٥﴾

**33-35.** የሰሩዋቸው ኃጢአቶች ለእነርሱ ይገለጹላቸዋል። ያም በእርሱ ይሳለቁበት የነበሩት ቅጣት በእነርሱ ላይ ይወርድባቸዋል። በዱንያ ይህንንም ቀናችሁን መገናኘትን እንደረሳችሁ ሁሉ ዛሬ እንተዋችኋለን። መኖሪያችሁም እሳት ናት። ለእናንተም ከረዳቶች ምንም የላችሁም ይባላል። ይህ እናንተ የአላህን አንቀፆች መቀላጃ አድርጋችሁ በመያዛችሁና ቅርቢቱን ሕይወት ስለ አታለለቻችሁ ነው ይባላሉ። ዛሬ ከእርሷ አይወጥጡም* እነርሱም በወቀሳ አይታለፉም።

✶ (ሀ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- «አንድ ሰው ወደ መቃብሩ ሲያመራ ሶስት ነገሮች ይከተሉታል። ሁለቱ ሲመለሱ አንዱ ግን ከርሱ ጋር ይቀራል። እነርሱም ቤተሰቡ፣ ንብረቱና የሰራው ስራ ሲሆኑ ቤተሰቡና ንብረቱ ሲመለሱ ስራው ግን ከርሱ ጋር ይቀራል።»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- «ሰዎች ሁሉ ወደ ጀሀነም እሳት ይወረወራሉ። ጀሀነምም «ተጨማሪ አለን?» ትላለች። ይህን ጊዜም የፍጥረታት ጌታ እግሮቹን ከእሷ ላይ ያስቀምጣል። የጀሀነም ጠርዞችም ሁሉም ወደ

አንድ ቦታ ይሰበሰባሉ። ጀሀነምም በዚህ ወቅት «በክብርህና በግርማ ሞገስህ ይሁን! ይብቃ! ይብቃ! ትላለች። ጀነትም ተጨማሪ ሰዎችን ለማስተናገድ ይበልጥ ትሰፋለች። አላህም ሌሎች ሰዎችን ፈጥሮ ጀነት እስከሚያስገባቸው ድረስም እንደሰፋች ትቀራለች።»

(ሐ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ይሉ ነበር:- «ካንተ በስተቀር አምልኮ የሚገባው አምላክ በሌለው ክብርህ እጠበቃለሁ። የሰው ልጆችና አጋንንቶች ሲሞቱ አንተ ብቻ ነህ የማትሞተው።»

فَلِلَّهِ ٱلْحَمْدُ رَبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَرَبِّ ٱلْأَرْضِ رَبِّ ٱلْعَٰلَمِينَ ٣٦
وَلَهُ ٱلْكِبْرِيَآءُ فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۖ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ٣٧

**36-37.** ምስጋና ሁሉ ለሰማያት፤ ለምድርና ለዓለማት ጌታ ለሆነው ለአላህ የተገባው ነው። ኩራትም በሰማያትም ሆነ በምድር ለእርሱ ብቻ ነው። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

### ከተንበርካኪዋ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-37) ካሉት አናቅፅ የምንማራቸው አንኳር ነጥቦች

1. ከአላህ የወረደ መሆኑን በመግለፅ ስለ ቁርኣን ትልቅነት ማውሳት፤
2. እምነት የቂን ከሚባለው የሰፋ መልዕክት ያለዉና በደረጃም እንደሚበልጥ መጠቆም፤
3. ንፁህ አዕምሮ ለኸይር ተግባር ካዋልነው ምን ያማረ መሆኑን፤
4. የአላህ ብቼኛ አምላክነት ማፅደቅን፤
5. ቁርኣን የብርሃኖች ሁሉ ብርሃን መሆኑንና በእሱ ያልተመለሰ በምንም ሊድን እንደሚቼል፤
6. አሉባልተኞችንና ወንጀለኞችን በከፉ ቅጣት መዛቱን፤
7. ከሰዎች ሁሉ መጥፎ ማለት የአላህን አንቀፅ ሰምቶ የሚያፌዝ መሆኑን፤
8. በክህደት ላይ ሁኖ የሞተ ሰው በዚህች ዐለም ሳለ ያፈራው ንብረትም ሆነ ዝናና ስልጣን ምንም እንደማይፈይዱት፤
9. ሰዎች በዚህች ዐለም ሳሉ ያመልኳቸው የነበሩት አማልክቶች፤ (መልአክ፤ ነቢያት፤ ወሊዮች) ሁሉ ምንም ሊፈይዱ እንደማይችሉ፤
10. ተውሒድን፤ ሙቶ መነሳትን፤ የአኺራን ምንዳና ነበይነትን በግልፅ ማረጋገጥ፤
11. አላህ ለሰው ልጆች ፀጋዉን የመስጠቱ ምክንያት እንዲያመሰግኑ መሆኑን፤
12. ከካፊሮች ጋር ይቅርታ መደራረግና በተለይ ሙስሊሞች በተዳከሙበት ዘመን የሚያደርሱትን ችግር እንኳን ሳይቀር እንደ ሁኔታው ማለፍ እንደሚቻል፤
13. ሰዎች በሌላ ሰው ወንጀል እንደማይጠየቅ፤
14. የመፅሐፍ ባለቤቶች የከፈሩት ነቢዩ ሙሐመድን ለመመቅኘት ነው፤
15. አላህ ለበኒ ኢስራኢል የሰጠው ክብር ምን ምን እንደሆነ።
16. ኢስላማዊ ህግን መተግበርና ከአንዱም ነጥብ እንኳን ቢሆን አለመደራደር፤
17. አላህ ለአማኙች ወዳጅ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የተንበርካኪዋ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (46)
# የአሻዋዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልአህቃፍ)

سُورَةُ الأَحۡقَافِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (35) ናቸው።
### የሱረቱ አል አሕቃፍ መግቢያ

ቁርኣን ከአላህ የወረደ መሆኑና በሱና ነብዩ (ﷺ) ማመን ግድ መሆኑን የሙቶ መነሳትንህቅነት፤ ካላፉት ሰዎች ቅጣት መማር እንደሚገባን ወላጆችን መንከባከብ ተገቢስ ለመሆኑ ቁርኣን ሲቀራ ሰምተው ያመኑት ጋኒኖች ታሪክ በአጭሩ አውስቶ ወደ መጨረሻው አካባቢ ላይ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ካፊሮች በሚያደርሱባቸው ስቃይና አዛ ሳይበገሩ በትዕግስት ማለፍ እንዳለባቸው በመምከር መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

حمٓ ١

1. *1ሓ፤ ሚይም፤*2

*1 ክፍል ሃያ ስድስተኛ

*2 (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

تَنزِيلُ ٱلۡكِتَٰبِ مِنَ ٱللَّهِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَكِيمِ ٢

2. የመጽሐፉ መወረድ አሸናፊ፤ ጥበበኛ ከሆነው ከአላህ ነው።

مَا خَلَقۡنَا ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَمَا بَيۡنَهُمَآ إِلَّا بِٱلۡحَقِّ وَأَجَلٖ مُّسَمّٗىۚ وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ عَمَّآ أُنذِرُواْ
مُعۡرِضُونَ ٣ قُلۡ أَرَءَيۡتُم مَّا تَدۡعُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ أَرُونِي مَاذَا خَلَقُواْ مِنَ ٱلۡأَرۡضِ أَمۡ لَهُمۡ شِرۡكٞ
فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِۖ ٱئۡتُونِي بِكِتَٰبٖ مِّن قَبۡلِ هَٰذَآ أَوۡ أَثَٰرَةٖ مِّنۡ عِلۡمٍ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٤

3-4. ሰማያትን፤ ምድርን እና በመካከላቸው ያለውን ሁሉ በምር እና በተወሰነ ጊዜንም በመለካት እንጂ ለቀልድ አልፈጠርናቸውም። እነዚያ በአላህ የካዱትም ከተስፈራሩት ነገር ትተው ዘዋሪዎች ናቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአላህ ሌላ የምትገዟቸውን አላያችሁምን? ከምድር ምንን እንደፈጠሩ

እስቲ አሳዩኝ። ወይም በሰማያት መፍጠር ለእነርሱ ከአላህ ጋር መጋራት አላቸውን? ያማልዱናል በማለታችሁ እውነተኞች እንደሆናችሁ ይህንን ጉዳይ ከዚህ በፊት የሆነን መጽሐፍ ወይም ከእውቀት እስቲ አምጡልኝ በላቸው።

وَمَنْ أَضَلُّ مِمَّن يَدْعُواْ مِن دُونِ ٱللَّهِ مَن لَّا يَسْتَجِيبُ لَهُۥٓ إِلَىٰ يَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ وَهُمْ عَن دُعَآئِهِمْ غَٰفِلُونَ ﴿٥﴾ وَإِذَا حُشِرَ ٱلنَّاسُ كَانُواْ لَهُمْ أَعْدَآءً وَكَانُواْ بِعِبَادَتِهِمْ كَٰفِرِينَ ﴿٦﴾

**5-6.** እስከ ትንሳኤ ቀን ድረስም ለእርሱ የማትመልስለትን ጣዖት ከአላህ ሌላ ከሚጠራ ሰው ይበልጥ የተሳሳተ ማንነው? እነርሱም ከጥሪያቸው ዘንጊዎች ናቸው። ሰዎችን በተሰበሰቡ ጊዜ ጣኦቶቹ ለእነርሱ ጠላቶች ይሆናሉ። እነርሱን መገዛታቸውንም ይክዳሉ።

وَإِذَا تُتْلَىٰ عَلَيْهِمْ ءَايَٰتُنَا بَيِّنَٰتٍ قَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِلْحَقِّ لَمَّا جَآءَهُمْ هَٰذَا سِحْرٌ مُّبِينٌ ﴿٧﴾ أَمْ يَقُولُونَ ٱفْتَرَىٰهُ ۖ قُلْ إِنِ ٱفْتَرَيْتُهُۥ فَلَا تَمْلِكُونَ لِى مِنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔا ۖ هُوَ أَعْلَمُ بِمَا تُفِيضُونَ فِيهِ ۚ كَفَىٰ بِهِۦ شَهِيدًۢا بَيْنِى وَبَيْنَكُمْ ۖ وَهُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلرَّحِيمُ ﴿٨﴾

**7-8.** በእነርሱም ላይ አንቀፆቻችን ግልፆች ሆነው በተነበቡ ጊዜ እነዚያ እውነቱን በመጣላቸው ጊዜ የካዱት ክፍሎች ይህ ግልፅ ድግምት ነው አሉ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይልቁን ሙሐመድ ራሱ ቀጠፈው ይላሉን? ብቀጥፈው ኖሮ እኔን ከአላህ ቅጣት ለማዳን አትችሉም። እርሱ ያንን የምትቀባዥሩበትን ነገር ሁሉ አዋቂ ነው። በእኔና በእናንተ መካከል መስካሪነት በእሱ በቃ። እርሱ መሀሪ እና አዛኝ ነው በላቸው።

قُلْ مَا كُنتُ بِدْعًا مِّنَ ٱلرُّسُلِ وَمَآ أَدْرِى مَا يُفْعَلُ بِى وَلَا بِكُمْ ۖ إِنْ أَتَّبِعُ إِلَّا مَا يُوحَىٰٓ إِلَىَّ وَمَآ أَنَا۠ إِلَّا نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٩﴾ قُلْ أَرَءَيْتُمْ إِن كَانَ مِنْ عِندِ ٱللَّهِ وَكَفَرْتُم بِهِۦ وَشَهِدَ شَاهِدٌ مِّنۢ بَنِىٓ إِسْرَٰٓءِيلَ عَلَىٰ مِثْلِهِۦ فَـَٔامَنَ وَٱسْتَكْبَرْتُمْ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٠﴾

**9-10.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመልዕክተኞች የተለየሁ ብጤ የሌለኝ አይደለሁም በእኔም በእናንተም ላይ ምን እንደሚሰራብንም አላውቅም። ወደ እኔ የሚወረደውን እንጂ ሌላን መመሪያ አልከተልም። እኔም ግልፅ አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እስቲ ንገሩኝ ቁርኣኑ ከአላህ ዘንድ ቢሆን እና በእርሱ ብትክዱ ከኢስራኤል ልጆች የሆነ መስካሪ በቢጤው ቢያምንና በእርሱ ላይ ቢመሰክርና እናንተ ብትኮሩም በዳይ አትሆኑምን? አላህ በእርግጥ በደለኛ ህዝቦችን ሁሉ አያቀናም በላቸው።

ከአሻዋዎች (9) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) የመካ ኑሮ በጣም በሙስሊሞች ላይ እንደ ከበደና በመናማቸው ዛፍ፤ ውሃ፤ቴምር፤ወደ ሞላበት ሀገር ሲሄዱ ስለ አዩ ለሶሃቦቻቸው ነገሯቸው ተደሰቱ። ሆኖም ያ መናም የታየው ጉዳይ ሳይረጋገጥ ብዙ ዘገየ የጓጉት ሶሃቦዎች መቼ ነው ወደዚያች ምድር የምንሰደደው እያሉ መጠየቅ ጀመሩ። እኔ ከአላህ የወረደልኝን ነው የምከተለው። በማለት ነብዩ ዝም አሉ።

وَقَالَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لِلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَوْ كَانَ خَيْرًا مَّا سَبَقُونَآ إِلَيْهِۚ وَإِذْ لَمْ يَهْتَدُواْ بِهِۦ فَسَيَقُولُونَ هَٰذَآ إِفْكٌ قَدِيمٌ ﴿١١﴾ وَمِن قَبْلِهِۦ كِتَٰبُ مُوسَىٰٓ إِمَامًا وَرَحْمَةًۚ وَهَٰذَا كِتَٰبٌ مُّصَدِّقٌ لِّسَانًا عَرَبِيًّا لِّيُنذِرَ ٱلَّذِينَ ظَلَمُواْ وَبُشْرَىٰ لِلْمُحْسِنِينَ ﴿١٢﴾

**11-12.** እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ስለ አመኑት ሰዎች እምነቱ መልካም ነገር በሆነ ኖሮ ወደ እርሱ ባልቀደሙን ነበር አሉ። በእርሱም ባልተቀኑ ጊዜ ይህ ቁርኣን ጥንታዊ ቅጥፈት ነው ይላሉ። ከፊቱም የሙሳን መጽሐፍ ለሰዎች መሪና የአላህ ፀጋ ሲሆን (እንዳወረድን አላየህምን?) ይህ ቁርኣን እነዚያን የበደሉትን ሊያስፈራራ በአረብኛ ቋንቋ የወረደ ሲሆን የፊቶቹንም መጽሐፍት አረጋጋጭ እና ለበጎ አድራጊዎችም ሁሉ የብስራት መጽሐፍ ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ قَالُواْ رَبُّنَا ٱللَّهُ ثُمَّ ٱسْتَقَٰمُواْ فَلَا خَوْفٌ عَلَيْهِمْ وَلَا هُمْ يَحْزَنُونَ ﴿١٣﴾ أُوْلَٰٓئِكَ أَصْحَٰبُ ٱلْجَنَّةِ خَٰلِدِينَ فِيهَا جَزَآءًۢ بِمَا كَانُواْ يَعْمَلُونَ ﴿١٤﴾

**13-14.** እነዚያ ጌታችን አላህ ነው ያሉና ከዚያ በዚሁ ቃላቸው ላይ ቀጥ ያሉ ሰዎች ሁሉ በእነርሱ ላይ ምንም ይደርስብናል ብለው ፍርሀት የለባቸውም። ምንም ነገር ያመልጠናል ብለው አያዝኑምም። እነዚያ የገነት ጓዶች ናቸው። በእርሷ ውስጥ ዘወታሪዎች ሲሆኑ በዚያ በዱንያ ይሰሩት በነበሩት መልካም ተግባር ምክንያት ታላቅን ምንዳ ይመነዳሉ።

ከአሻዋዎች ምዕራፍ (11-14) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የመካ ካፊሮች ብዙ አማኞች ድሃዎች ሆነው ስላዮቸው ማለትም አማር፤ ቢላል፤ አብደላህ ኢብኑ መስዑድ እና መሰሎቹ ባዩ ጊዜ ይህን ቃል ስለተናገሩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

**ከአሻዋዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-14) ከምናገኛቸውአንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ቁርኣን በነብዩ (ﷺ) አማካኝነት ከአላህ የወረደ መሆኑን በመግለፅ የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
2. የአላህ በሰማይና በምድር እንዲሁም በመካከል ያሉትን በመፍጠርም ሆነ በተለያዩ ተግባራቱ ከቀልድና ፌዝ የፀዳ መሆኑን፤
3. አንድት ከክለኛ ሳይንሳዊ እውነታን ማረጋገጥ ይኸው ያለፈጣሪ አይመለከም የሚል ምንም ነገር ሊፈፅምለት የማይችለውን ጣኦት ዛፍ፤ ቀብር የመሳሰሉ ነገሮችን በተወሱል ስም ከሚያመልክ የበለጠ የተሳሳተ እንደሌለ፤
4. መኮች ቁርኣን ድግምት ነው ብለው ለማስተባበል ሞክረዋል፤
5. ነብዩ (ﷺ) የቀጣጠፈው ነው ብለዋቸው እንደነበር፤
6. ነብዩ (ﷺ) እንደሌሎች ነብያት ገይብ እንደማያውቁ በግልፅ ማስረዳታቸው፡፡
7. ከተወረደላቸውበስተቀርመጨመርምሆነመቀነስእንደማይችሉ፤
8. የነብዩ ተልዕኮና ኃላፊነት በግልፅ ማስተማር ብቻ መሆኑን ቁርኣን በነብዩ ሙሐመድ አማካኝነት ከአላህ የወረደ መሆኑን በመግለፅ የነብዩሙሐመድን ነብይነት ማረጋገጥ፤
9. እውነትን ለማግኘት ምስክር አንዱ መንገድ መሆኑንና ለምስክርነት የሚቀርቡ ሁሉ አዲል ከታላላቅ ወንጀሎች ሁሉ የራቀና ከጥቃቅን ወንጀሎች ከአብዛኛው የራቀ መሆን እንዳለበት፤
10. የሰው ልጅ ለማያውቀው ነገር ሁሉ ጠላት እንደሆነ ማረጋገጥ፤
11. ቁርኣንና ኦሪት ምን ያህል ግንኙነት እንዳላቸውና አንዱ ለሌላው ምስክር መስጠቱ ይበልጥ እንደሚጠቅም፤
12. ኢስላማዊ ትምህርት በትክክልና በአግባብ ለማስተማር የፈለገ ሰው አረብኛ ቋንቋን መማር ግዴታ እንደሆነ፤
13. ኢስቲቃማ አስፈላጊ መሆኑን እንማራለን፡፡

وَوَصَّيْنَا ٱلْإِنسَـٰنَ بِوَٰلِدَيْهِ إِحْسَـٰنًا ۖ حَمَلَتْهُ أُمُّهُۥ كُرْهًا وَوَضَعَتْهُ كُرْهًا ۖ وَحَمْلُهُۥ وَفِصَـٰلُهُۥ
ثَلَـٰثُونَ شَهْرًا ۚ حَتَّىٰٓ إِذَا بَلَغَ أَشُدَّهُۥ وَبَلَغَ أَرْبَعِينَ سَنَةً قَالَ رَبِّ أَوْزِعْنِىٓ أَنْ أَشْكُرَ نِعْمَتَكَ
ٱلَّتِىٓ أَنْعَمْتَ عَلَىَّ وَعَلَىٰ وَٰلِدَىَّ وَأَنْ أَعْمَلَ صَـٰلِحًا تَرْضَىٰهُ وَأَصْلِحْ لِى فِى ذُرِّيَّتِىٓ ۖ إِنِّى تُبْتُ
إِلَيْكَ وَإِنِّى مِنَ ٱلْمُسْلِمِينَ ﴿١٥﴾ أُو۟لَـٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ نَتَقَبَّلُ عَنْهُمْ أَحْسَنَ مَا عَمِلُوا۟ وَنَتَجَاوَزُ
عَن سَيِّـَٔاتِهِمْ فِىٓ أَصْحَـٰبِ ٱلْجَنَّةِ ۖ وَعْدَ ٱلصِّدْقِ ٱلَّذِى كَانُوا۟ يُوعَدُونَ ﴿١٦﴾

**15-16.** የሰውን ልጅ ለወላጆቹ በጎ መዋል እንዳለበት በጥብቅ አዘዝነው፡፡ እናቱ በችግርም ላይ ሆና አረገዘችው፡፡ በችግርም ላይ ሆና ወለደችው፡፡ እርግዝናውና ከጡት መለያው ሙሉ ሰላሳ ወር ነው፡፡ ከዚያ የጥንካሬውን

ወቅት በደረሰ ጊዜ (አርባ ዓመት) በደረሰ ጊዜ ጌታዬ ሆይ! ያን በእኔ ላይና በወላጆቼ ላይ የለገስከዉን ፀጋን እንድናመሰግንህና የምትወደውን መልካም ስራ እንድሰራ ወደ ቀናው መንገድ ምራኝ። ዘሮቼንም ለእኔ አብጅልኝ። እኔ ወደ አንተ ብቻ ተመለስኩ። እኔ ከሙስሊሞች አንዱ ነኝ አለ። እነዚህ (ይህንን ባዩች) ሁሉ ከገነት ጓዶች ውስጥ ሲሆኑ እነዚያ ከሰሩት ስራ መልካሙን የምንቀበላቸውና ከኃጢአቶቻቸውም የምናልፋቸው ሰዎች ናቸው። ያንን ተስፋ ይሰጡት የነበሩትን እውነተኛ ቀጠሮ እንሞላላቸዋለን።

وَٱلَّذِى قَالَ لِوَٰلِدَيۡهِ أُفّٖ لَّكُمَآ أَتَعِدَانِنِيٓ أَنۡ أُخۡرَجَ وَقَدۡ خَلَتِ ٱلۡقُرُونُ مِن قَبۡلِي وَهُمَا يَسۡتَغِيثَانِ ٱللَّهَ وَيۡلَكَ ءَامِنۡ إِنَّ وَعۡدَ ٱللَّهِ حَقّٞ فَيَقُولُ مَا هَٰذَآ إِلَّآ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿١٧﴾ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ حَقَّ عَلَيۡهِمُ ٱلۡقَوۡلُ فِيٓ أُمَمٖ قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلِهِم مِّنَ ٱلۡجِنِّ وَٱلۡإِنسِۖ إِنَّهُمۡ كَانُواْ خَٰسِرِينَ ﴿١٨﴾

**17-18.** ያን ሁለቱ ወላጆቹ አላህን የሚለምኑ ሲሆኑ ወዬልህ በአላህ እመን፤ የአላህ ቀጠሮ እርግጠኛ ነው፤ ሲሉት ኡፍ እናንተኮ ከእኔ በፊት የብዙ ክፈለ ዘመናት ሰዎች ሳይወጡ በእርግጥ ያለፉ ሲሆኑ ከመቃብር እንደምወጣ ታስፈራሩኛላችሁን እነዚህ ከአጋንንትም ከሰውም ከእነርሱ በፊት ከአለፉት ህዝቦች ጋር የአላህ ቃሉ በእነርሱ ላይ የተረጋገጠባቸው ናቸው። እነርሱ ከሳሪዎች ነበሩና።

وَلِكُلّٖ دَرَجَٰتٞ مِّمَّا عَمِلُواْۖ وَلِيُوَفِّيَهُمۡ أَعۡمَٰلَهُمۡ وَهُمۡ لَا يُظۡلَمُونَ ﴿١٩﴾ وَيَوۡمَ يُعۡرَضُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ عَلَى ٱلنَّارِ أَذۡهَبۡتُمۡ طَيِّبَٰتِكُمۡ فِي حَيَاتِكُمُ ٱلدُّنۡيَا وَٱسۡتَمۡتَعۡتُم بِهَا فَٱلۡيَوۡمَ تُجۡزَوۡنَ عَذَابَ ٱلۡهُونِ بِمَا كُنتُمۡ تَسۡتَكۡبِرُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ بِغَيۡرِ ٱلۡحَقِّ وَبِمَا كُنتُمۡ تَفۡسُقُونَ ﴿٢٠﴾

**19-20.** ለሁሉም በሰሩት ስራ ልክ ተገቢ የሆኑ ደረጃዎች አሏቸው። ስራዎቻቸውንም ይሞላላቸው ዘንድ ይህን መነዳቸው። እነርሱም አይበደሉም። እነዚያም በአላህ የካዱት በእሳት ላይ በሚጋፈጡበት ቀን ጣፋጮቻችሁን በአነስተኛይቱ ሕይወታችሁ አሳለፋችሁ። በእርሷም ተጣቀማችሁ ስለዚህ በምድር ላይ ያለ አግባብ ትኮሩ በነበራችሁትና ታመፁ በነበራችሁት ምክኒያት ዛሬ የውርደትን ቅጣት ትመነዳላችሁ ይባላሉ።

**ከአሻዋዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (15-20) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የወላጆችን ሀቅ ክብደትና ምን ምን ማድረግ እንደሚገባ፤
2. የእርግዝና እድሜ ከ (60) አንስቶ ከዚያም በላይ ሊሆን እንደሚቻልና የማጥቢያ ጊዜ ሁለት ዓመትና ከዚያም በታች ሊሆን እንደሚችል፤
3. በንስሀና የአላህን ትዕዛዝ በማክበር ወደ አላህ መቃረብ ተገቢ መሆኑን፤
4. የአቡበክር ቤተሰቦች ያለው ትልቅ ማዕረግና የጀነት ሰዎች መሆናቸውን ማብሰር፤
5. የወላጆችን ሀቅ መርገጥና መጣስ ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
6. ወላጆች ለልጆቻቸው ያላቸው ከፍተኛ ፍቅር የሚከፍሉት መስዋዕትነት፤
7. በአልሆኑ ምኞቶችና የግል ፍላጎት ላይ ጠልቆ ከመግባት ማስጠንቀቅ፤

۞ وَٱذۡكُرۡ أَخَا عَادٍ إِذۡ أَنذَرَ قَوۡمَهُۥ بِٱلۡأَحۡقَافِ وَقَدۡ خَلَتِ ٱلنُّذُرُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ
وَمِنۡ خَلۡفِهِۦٓ أَلَّا تَعۡبُدُوٓاْ إِلَّا ٱللَّهَ إِنِّيٓ أَخَافُ عَلَيۡكُمۡ عَذَابَ يَوۡمٍ عَظِيمٖ ﴿٢١﴾
قَالُوٓاْ أَجِئۡتَنَا لِتَأۡفِكَنَا عَنۡ ءَالِهَتِنَا فَأۡتِنَا بِمَا تَعِدُنَآ إِن كُنتَ مِنَ ٱلصَّٰدِقِينَ ﴿٢٢﴾
قَالَ إِنَّمَا ٱلۡعِلۡمُ عِندَ ٱللَّهِ وَأُبَلِّغُكُم مَّآ أُرۡسِلۡتُ بِهِۦ وَلَٰكِنِّيٓ أَرَىٰكُمۡ قَوۡمٗا تَجۡهَلُونَ ﴿٢٣﴾
فَلَمَّا رَأَوۡهُ عَارِضٗا مُّسۡتَقۡبِلَ أَوۡدِيَتِهِمۡ قَالُواْ هَٰذَا عَارِضٞ مُّمۡطِرُنَاۚ بَلۡ هُوَ مَا ٱسۡتَعۡجَلۡتُم بِهِۦۖ
رِيحٞ فِيهَا عَذَابٌ أَلِيمٞ ﴿٢٤﴾ تُدَمِّرُ كُلَّ شَيۡءِۭ بِأَمۡرِ رَبِّهَا فَأَصۡبَحُواْ لَا يُرَىٰٓ إِلَّا مَسَٰكِنُهُمۡۚ
كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡمُجۡرِمِينَ ﴿٢٥﴾

**21-25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሕዝቦችን በአል አህቃፍ ይኖሩ የነበሩ የዓድ ህዝቦች ወንድም የሆነው ሁድ ከእርሱ በፊትም ሆነ ከእርሱ በኋላ አስፈራሪዎች ተልከው የነበሩ ሲሆን ከአላህ ውጪ ሌሎች አማልክትን አታምልኩ። የታላቁን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ በማለት ሲያስጠነቅቃቸው ከአማልክቶቻችን ልታሸሸን መጣህን? እውነተኛ ከሆንክ ያ የምታስፈራራን ቅጣት አሁን እንዲከሰት አድርግ አሉት። የቅጣቱ መከሰቻ ትክክለኛ ወቅት እውቀት ያለው ከአላህ ዘንድ ብቻ ነው። የተላኩበትን መልዕክት ብቻ አደርስላችኋለሁ። ግና እንደማያችሁ መሀይማን ህዝቦች ናችሁ አላቸው። ለቅጣት የተላከባቸውን ዳመና ወደ ሸለቆዎቻቸው አቅጣጫ ሲጓዝ ባዩ ጊዜ ይህ ዝናብ የሚያወርድልን ዳመና ነው አሉ። ሁድም ይልቁንም ያ በፍጥነት ይከሰት ዘንድ የጠየቃችሁት ቅጣት ነው። አሳማሚ ቅጣት ያዘለ ነፋስ ነው አለ። በጌታው ትዕዛዝ ሁሉን ነገር አውድሟል አላቸው። ባዶ ቤቶቻቸው እንጂ ሌላ ነገር የማይታይ ሆኖው አነጉ። አመፀኞች ህዝቦችን በዚህ መልኩ እንቀጣለን።

وَلَقَدْ مَكَّنَّٰهُمْ فِيمَآ إِن مَّكَّنَّٰكُمْ فِيهِ وَجَعَلْنَا لَهُمْ سَمْعًا وَأَبْصَٰرًا وَأَفْـِٔدَةً فَمَآ أَغْنَىٰ
عَنْهُمْ سَمْعُهُمْ وَلَآ أَبْصَٰرُهُمْ وَلَآ أَفْـِٔدَتُهُم مِّن شَىْءٍ إِذْ كَانُوا۟ يَجْحَدُونَ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِ وَحَاقَ
بِهِم مَّا كَانُوا۟ بِهِۦ يَسْتَهْزِءُونَ ٢٦

**26.** (ቁረይሾች ሆይ)፣ በዚያም ለእናንተ በርሱ ያልሰጠነውን ኃይልና ምቾት ለእነርሱ ሰጥተናል። መስሚያ ጆሮዎችን፤ መመልከቻ ዓይኖችን እና ማሰቢያ አእምሮንም ለግሰናቸዋል። ግና ጆሮዎቻቸውም፤ ዓይኖቻቸውም፤ አእምሮዎቻቸውም የፈየዱቸው ነገር አልነበረም። የአላህን አናቅፅ ያስተባብሉ ነበርና። በመሆኑም በዚያ ያፌዙበት በነበረው ቅጣት ወረደባቸው።

وَلَقَدْ أَهْلَكْنَا مَا حَوْلَكُم مِّنَ ٱلْقُرَىٰ وَصَرَّفْنَا ٱلْـَٔايَٰتِ لَعَلَّهُمْ يَرْجِعُونَ ٢٧ فَلَوْلَا نَصَرَهُمُ
ٱلَّذِينَ ٱتَّخَذُوا۟ مِن دُونِ ٱللَّهِ قُرْبَانًا ءَالِهَةًۢ بَلْ ضَلُّوا۟ عَنْهُمْ وَذَٰلِكَ إِفْكُهُمْ وَمَا كَانُوا۟ يَفْتَرُونَ ٢٨

**27-28.** በዙሪያቸው የነበሩ ከተሞችንም አጠፋን። (ከክህደታቸው) ይመለሱ ዘንድ ተደጋጋሚ ታዐምራትን አሳይተናቸው ነበር። እነዚያ መቃረቢያ ይሆናቸው ዘንድ ከአላህ ሌላ በረዳትነት የያዟቸው አማልዕክት በመከራቸው ወቅት ለምን አይረዷቸውም ኖሯልን? ይልቁንም ከእነርሱ ራቁ። ይህ ሀሰታቸውና ይቀጥፉት የነበረው ነውና።

وَإِذْ صَرَفْنَآ إِلَيْكَ نَفَرًا مِّنَ ٱلْجِنِّ يَسْتَمِعُونَ ٱلْقُرْءَانَ فَلَمَّا حَضَرُوهُ قَالُوٓا۟ أَنصِتُوا۟ فَلَمَّا قُضِىَ
وَلَّوْا۟ إِلَىٰ قَوْمِهِم مُّنذِرِينَ ٢٩ قَالُوا۟ يَٰقَوْمَنَآ إِنَّا سَمِعْنَا كِتَٰبًا أُنزِلَ مِنۢ بَعْدِ مُوسَىٰ مُصَدِّقًا
لِّمَا بَيْنَ يَدَيْهِ يَهْدِىٓ إِلَى ٱلْحَقِّ وَإِلَىٰ طَرِيقٍ مُّسْتَقِيمٍ ٣٠ يَٰقَوْمَنَآ أَجِيبُوا۟ دَاعِىَ ٱللَّهِ وَءَامِنُوا۟
بِهِۦ يَغْفِرْ لَكُم مِّن ذُنُوبِكُمْ وَيُجِرْكُم مِّنْ عَذَابٍ أَلِيمٍ ٣١ وَمَن لَّا يُجِبْ دَاعِىَ ٱللَّهِ فَلَيْسَ
بِمُعْجِزٍ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَيْسَ لَهُۥ مِن دُونِهِۦٓ أَوْلِيَآءُ أُو۟لَٰٓئِكَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ٣٢

**29-32.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአጋንንት የሆኑ ጭፍሮች ቁርኣንን ያደምጡ ዘንድ በላክንልህ ጊዜ የሆነውን (አስታውስ)። ሲነበብ በደረሱ ጊዜ ዝም በሉ ተባባሉ። ንባቡ ሲጠናቀቅም ወገኖቻቸውን ለማስጠንቀቅ ወደ መጡበት ተመለሱ። አሉም ለወገኖቻቸው ወገኖቻችን ሆይ! ከሙሳ ተውራት በኋላ የተዋረደንና ከእርሱ በፊት የወረዱትን መጽሐፍት አፅዳቂ ወደ እውነትና ወደ ቀጥተኛው ጎዳና መሪም የሆነን መጽሐፍ አደመጥን። ወገኖቻችን ሆይ! ለእዚህ ወደ አላህ ለሚጠራችሁ ሰው በጎ ምላሽ ስጡ። በእርሱ እመኑም።

ይህን ካረጋችሁ አላህ ኃጢአቶቻችሁን ይምርላችኋል ከአሳማሚ ቅጣትም ይጠብቃችኋል። ወደ አላህ ለሚጠራ ሰው በጎ ምላሽ ያልሰጠ በምድር ላይ ከአላህ ቅጣት አያመልጥም። ከእርሱ ሌላም ረዳት አይኖረውም። እንዲህ አይነት ሰዎች ግልፅ ጥመት ውስጥ ናቸው።

ከአሻዋዎች ምዕራፍ (29) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) የነኽላ ሸለቆ በተባለው ቦታ ሆነው ቁርኣን እያነበቡ ባለበት አንድ ከዘጠና የማያንስ የጅን ቡድን መጣ። የእሳቸውን ንባብ በሰማም ጊዜ በደንብ አዳምጦ ወደ ህዝቦቹ ተመለሰ የሰማውን ተናገረ። ጅኖች ወደ ነብዩ (ﷺ) በመጡበት ጊዜ ከስድስት ጊዜ የማያንስ መሆኑን ብዛት ያላቸው የሃይማኖት ምሁራን ዘግበዋል። ከነዚህ መሀከል አንዱ አጋጣሚ በዚህ አንቀፅ የተጠቀሰ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በአልጅን የተጠቀሰው ክስተት ነው።

أَوَلَمۡ يَرَوۡاْ أَنَّ ٱللَّهَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ وَلَمۡ يَعۡيَ بِخَلۡقِهِنَّ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يُحۡـِۧيَ ٱلۡمَوۡتَىٰۚ بَلَىٰٓۚ إِنَّهُۥ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٞ ٣٣

33. ያ! ሰማያትንና ምድርን የፈጠረው እርሱም በመፍጠሩም ድካም ያልተሰማው አላህ ሙታንን ህያው ማድረግ እንደሚችል አላዩምን? በእርግጥም ይህን ማድረግ የሚሳነው አይደለም። እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነውና።

وَيَوۡمَ يُعۡرَضُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ عَلَى ٱلنَّارِ أَلَيۡسَ هَٰذَا بِٱلۡحَقِّۖ قَالُواْ بَلَىٰ وَرَبِّنَاۚ قَالَ فَذُوقُواْ ٱلۡعَذَابَ بِمَا كُنتُمۡ تَكۡفُرُونَ ٣٤

34. እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ሁሉ ወደ እሳት እንዲቀርቡ በሚደረጉ ጊዜ የሚሆነውን አስታውስ። ይህ እውነት አይደለምን? ይባላሉ። አዎ እውነት መሆኑን በጌታችን በመማል እናረጋግጣለን ይላሉ። እርሱም ታስተባብሉት በነበራችሁት ሰበብ ቅጣትን ቅመሱ ይላቸዋል።

فَٱصۡبِرۡ كَمَا صَبَرَ أُوْلُواْ ٱلۡعَزۡمِ مِنَ ٱلرُّسُلِ وَلَا تَسۡتَعۡجِل لَّهُمۡۚ كَأَنَّهُمۡ يَوۡمَ يَرَوۡنَ مَا يُوعَدُونَ لَمۡ يَلۡبَثُوٓاْ إِلَّا سَاعَةٗ مِّن نَّهَارِۭۚ بَلَٰغٞۚ فَهَلۡ يُهۡلَكُ إِلَّا ٱلۡقَوۡمُ ٱلۡفَٰسِقُونَ ٣٥

35. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመልዕክተኞች የፅናት ባለቤቶች እንደታገሱት ሁሉ አንተም ታገስ። ቅጣቱ ይፋጠንባቸው ዘንድም አትጠይቅ። ያን ቃል የተገባላቸውን ቅጣት በሚያዩ ጊዜ ምድር ላይ ከቀን ውስጥ የተወሰነ ወቅት ብቻ እንጂ እንዳልቆዩ ይሰማቸዋል። ይህ የማስጠንቀቂያ መልዕክት ነው። ከአመፀኞች ህዝቦች ውጪ ሌሎች እንዲጠፉ ይደረጋልን?

**ከአሻዋዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (21-35) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የመካ ሰዎች በነብዩ ላይ የነበራቸው አመለካከት ልክ የዓድ ሰዎች በነብያቸው በሁድ ላይ የነበራቸው አመለካከት እንደሚመስል፤
2. ወደ ኢስላም ጥሪ የሚያደርግ ሁሉ በመልካም በመጥራትና በጥበብ በማስተማር የነብዩን (ﷺ) ፈለግ መከተል እንዳለበት፤
3. ባለ ጉልበት በጉልበቱ፤ ባለሀብት በሀብቱ፤ ባለ እውቀት በእውቀቱ ሳይታለል አላህ ቢፈልግ አለኝ ብሎ የሚንቦጣረርበትን በአፍታ መውሰድ እንደሚችል፤
4. ንፋስ ዳመና እንደሌላው የዚህ ዓለም እንቅስቃሴ ሁሉ በጌታቸው ትዕዛዝ ብቻ እንደሚንቀሳቀሱ፤
5. የቁርኣን ትልቅነት፤
6. ጅኖች ቁርኣንን በአንድ ቀን ሰምተው የዚያን ያክል መመሰጥ ሲችሉ ለብዙ ጊዜ የሰሙት የሰው ልጆች አለመቀበላቸው የሚገርምና የሚደንቅ መሆኑን፤
7. ይህ ዓለም ራሱና በውስጡ ያሉት እንቅስቃሴዎች አላህ ለመኖሩ ግልፅ ማስረጃ መሆናቸውን፤
8. ጅን የሚባል ፍጡር መኖሩ የሚያጠራጥር አለመሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የአሻዋዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (47)
# የሙሐመድ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ሙሐመድ)

سُورَةُ مُحَمَّدٍ

**የወረደው በመዲና ነው። የአናቅፅ ብዛት (38) ናቸው።**
**የሱረቱ ሙሐመድ መግቢያ**

በመነሻው አላህ የከሓዲያንን ተግባር እንዳበላሸና ለሙዕሚኖች ወንጀላቸውን እንዳበሰላቸው በማብሰር ነው የሚጀምረው። በተደጋጋሚ ሀቅን መከተል እንዳለብን በማሳሰብ የዚሁ ምንዳ ጀነት መግባት መሆኑን ይገልፃል።

የአላህን ዲን በመርዳትና በጅሀድ ላይ ግፊት ያሳድራል። ከሓዲያን ከእምነት ከሸሹ ምድርን በጥፋት እንደሚበክሉና ዝምድናን እንደሚቆርጡ ግልፅ አስመሳዮች እንዳያሳንፉ ከአማኞች ጋር መሆን እንደሌላባቸው ያስጠነቅቃል። አስመሳዮችን ከአስፈላጊ ሚስጥራቸው ለነብዩ (ﷺ) አግልጦ ሊሰጥባቸው እንደሚችል ያስፈራራል። አማኞች አላህ አብሮአቸው ስላለና የበላዩቹ ድል አድራጊዎች እነሱ በመሆናቸው ከሓዲያንን ከመዋጋት እንዳይሳነፉ ያስጠነቅቃል። በመጨረሻም ለአላህ ብሎ ገንዘብን ማውጣትና እስከ ሕይወት መስዋዕትነትን በመክፈል አስፈላጊነቱን በመግለፅ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ أَضَلَّ أَعۡمَٰلَهُمۡ ١ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ
ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَءَامَنُواْ بِمَا نُزِّلَ عَلَىٰ مُحَمَّدٖ وَهُوَ ٱلۡحَقُّ مِن رَّبِّهِمۡ كَفَّرَ عَنۡهُمۡ سَيِّـَٔاتِهِمۡ
وَأَصۡلَحَ بَالَهُمۡ ٢ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ ٱتَّبَعُواْ ٱلۡبَٰطِلَ وَأَنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّبَعُواْ ٱلۡحَقَّ
مِن رَّبِّهِمۡۚ كَذَٰلِكَ يَضۡرِبُ ٱللَّهُ لِلنَّاسِ أَمۡثَٰلَهُمۡ ٣

**1-3.** እነዚያ በአላህ የካዱ እና ከአላህ መንገድ ሌሎችን የከለከሉ አላህ ስራዎቻቸውን* አጠፋባቸው። እነዚያም በአላህ ያመኑ በጎዎችንም ተግባራት የሰሩ በሙሐመድ ላይም በተወረደው እርሱ ከጌታቸው ሲሆን እውነት ስለሆነ ያመኑ ከእነርሱ ላይ ኃጢአቶቻቸውን ያብሳል። ሁኔታቸውንም ሁሉ ያበጃል። ይህ እነዚያ በአላህ የካዱት ውሸትን የተከተሉ በመሆናቸውና እነዚያም በአላህ ያመኑት ከጌታቸው የሆነን እውነት ስለተከተሉ ነው። እንደዚሁ አላህ ለሰዎች ምሳሌዎቻቸውን ያብራራል።

ከሙሐመድ ምዕራፍ ከ (1-2) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- የመካ ካፊሮችና እና የመዲና ሙስሊሞችን አስመልክቶ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (ሱዩጢ)

✷ ይህ አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ኢብኑ አባስ እንዳሉት በበድር ዘመቻ ዕለት የካፊሮቹን ወጪ ሸፍነው የነበሩ አስራ ሁለት ሰዎችን ምክንያት በማድረግ ነው ብለዋል። መልዕክቱም በአላህና በመልዕክተኛው የካዱ ሰዎች ሁሉ ምንም ያህል በጎ ተግባር ቢያደርጉ ተቀባይነት እንደሌላቸው እና ዋናው ቁልፉ በአላህም እንኳን ቢያኑ በነብዩ ካላመኑ ፋይዳ እንደሌላቸው ያመለክታል ይህን አበባል ነበር ነብዩ እንዲህ ሲሉ የገለፁት ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ! ከጀሀነም ሰዎች ካልሆነ በስተቀር በአይሁድና ክርስቲያኖች መካከል ስለ እኔ ሰምቶ እኔ በተላኩበት መልዕክት ሳያምን የሚቀር የለም»

فَإِذَا لَقِيتُمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ فَضَرْبَ ٱلرِّقَابِ حَتَّىٰٓ إِذَآ أَثْخَنتُمُوهُمْ فَشُدُّوا۟ ٱلْوَثَاقَ فَإِمَّا مَنًّۢا
بَعْدُ وَإِمَّا فِدَآءً حَتَّىٰ تَضَعَ ٱلْحَرْبُ أَوْزَارَهَا ۚ ذَٰلِكَ ۖ وَلَوْ يَشَآءُ ٱللَّهُ لَٱنتَصَرَ مِنْهُمْ وَلَٰكِن
لِّيَبْلُوَا۟ بَعْضَكُم بِبَعْضٍ ۗ وَٱلَّذِينَ قُتِلُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ فَلَن يُضِلَّ أَعْمَٰلَهُمْ ﴿٤﴾ سَيَهْدِيهِمْ
وَيُصْلِحُ بَالَهُمْ ﴿٥﴾ وَيُدْخِلُهُمُ ٱلْجَنَّةَ عَرَّفَهَا لَهُمْ ﴿٦﴾

**4-6.** (አማኞች ሆይ)፣ እነዚያንም በአላህ የካዱትን ሰዎች በጦር ላይ በአገኛችኋቸው ጊዜ ጫንቃዎችን በሀይል ምቱ። ባደከማችኋቸው ጊዜም አትግደሏቸው ማርኳቸው። ማሰሪያውንም አጥብቁ። በኋላም ወይም በነጻ ትለቁቸዋላችሁ። ወይም ፊዳ ታስከፍሏቸዋላችሁ። ይህም ጦሩ መሳሪያዉን እስከሚጥል ድረስ ነው። ነገሩ ይህ ነው። አላህም ቢፈልግ ከእነርሱ ያለ ጦር በተበቀለ ነበር ግን ከፊላችሁን በከፊሉ ሊሞክር (በዚህ አዘዛችሁ)። እነዚያንም በአላህ መንገድ ላይ የተገደሉትን ሰዎች ስራዎቻቸውን ፈፅሞ አያጠፋባቸውም። በእርግጥ ይመራቸዋል። ሁኔታቸውንም ሁሉ ያበጃል። ገነትንም ያስገባቸዋል። ለእነርሱ አስታወቋታል።✷

✷ የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «ምእመናን ከጀሃነም እሳት ከተጠበቁ በኋላ በጀሀነምና በጀነት መካከል ባለው ድልድይ ላይ ይሆኑና በምድር ላይ አንዳቸው አንዳቸውን ለበደለው ከሳ እንዲመልስ ይዳረጋል። ሁሉም ካለባቸው ካሳ ከጠሩትና ከፀዱ በኋላ ጀነት እንዲገቡ ይፈቀድላቸው። የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! ከነርሱ መካከል እያንዳንዱ በጀነት ውስጥ ያለው መኖሪያው ምድር ላይ ከነበረው መኖሪያው የተሻለ እንደሆነ ያውቃል።»

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِن تَنصُرُوا۟ ٱللَّهَ يَنصُرْكُمْ وَيُثَبِّتْ أَقْدَامَكُمْ ﴿٧﴾ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟
فَتَعْسًا لَّهُمْ وَأَضَلَّ أَعْمَٰلَهُمْ ﴿٨﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ كَرِهُوا۟ مَآ أَنزَلَ ٱللَّهُ فَأَحْبَطَ أَعْمَٰلَهُمْ ﴿٩﴾

**7-9.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሆይ፣ የአላህን ሃይማኖት ብትረዱ ይረዳችኋል። ጫማዎቻችሁንም ያደላድላል። እነዚያም የካዱት ለእነርሱ ጥፋት ተገባቸው። ስራዎቻቸውንም አጠፋባቸው። ይህ እነርሱ አላህ ያወረደውን ስለጠሉ ነው። ስለዚህ ስራዎቻቸውን አበላሸባቸው።

ከሙሐመድ ምዕራፍ (8) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በኡሑድ ዕለት ሙሽሪኮች ሁበል ደስ ይበልህ ንገስ ስላሉ ሙስሊሞች አላህ የበለጠ የነገሰ ነው በማለት ሲነገሩ ሙሽሪኮች ለእኛ ኡዛ አለን ለእናንተ ግን ኡዛ የላችሁም ሲሉ ነብዩ ጌታችን አላህ ነው እናንተ ጌታ የላችሁም በሏቸው ስላሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)።

۞ أَفَلَمۡ يَسِيرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ فَيَنظُرُواْ كَيۡفَ كَانَ عَٰقِبَةُ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۖ دَمَّرَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِمۡۖ
وَلِلۡكَٰفِرِينَ أَمۡثَٰلُهَا ١٠ ذَٰلِكَ بِأَنَّ ٱللَّهَ مَوۡلَى ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَأَنَّ ٱلۡكَٰفِرِينَ لَا مَوۡلَىٰ
لَهُمۡ ١١ إِنَّ ٱللَّهَ يُدۡخِلُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُۖ
وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يَتَمَتَّعُونَ وَيَأۡكُلُونَ كَمَا تَأۡكُلُ ٱلۡأَنۡعَٰمُ وَٱلنَّارُ مَثۡوٗى لَّهُمۡ ١٢

**10-12.** የእነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩ ከሓዲያን ሁሉ መጨረሻ እንዴት እንደነበር ያዩ ዘንድ በምድር ላይ አልሄዱምን? አላህ ያላቸውን ሁሉ አጠፋባቸው ለካሓዲያንም ሁሉ የዚሁ ተመሳሳይ አሉላቸው። ይህ አላህ የእነዚያ ያመኑትን ሰዎች ረዳት ስለሆነና ከሓዲያንም ለእነርሱ ረዳት ስሌላቸው ነው። አላህ እነዚያን በእሱ ያመኑትንና መልካሞችን ተግባራት የሰሩትን ሁሉ ከስሮቻቸው ወንዞች ወደ ሚፈሱባቸው ገነቶች ያስገባቸዋል። እነዚያም በአላህ የካዱትን ሁሉ በቅርቢቱ ዓለም ብቻ ይጣቀማሉ። እንስሳዎችም እንደሚበሉ ይበላሉ። የገሀነም እሳትም ለእነርሱ የሁል ጊዜ መኖሪያቸው ናት።

وَكَأَيِّن مِّن قَرۡيَةٍ هِيَ أَشَدُّ قُوَّةٗ مِّن قَرۡيَتِكَ ٱلَّتِيٓ أَخۡرَجَتۡكَ أَهۡلَكۡنَٰهُمۡ فَلَا نَاصِرَ لَهُمۡ ١٣
أَفَمَن كَانَ عَلَىٰ بَيِّنَةٖ مِّن رَّبِّهِۦ كَمَن زُيِّنَ لَهُۥ سُوٓءُ عَمَلِهِۦ وَٱتَّبَعُوٓاْ أَهۡوَآءَهُم ١٤

**13-14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከዚያች አንተን ካወጣችህ ከተማህ ይበልጥ በሀይል ጠንካራ የሆኑ ባለቤቶቻቸዉን ያጠፋናቸው ብዙ ናቸው። ለእነርሱም ረዳት አልነበራቸውም። ከጌታው በሆነች አስረጅ ላይ የሆነ ምዕመን ክፉ ስራቸው ለእነርሱ እንደተሸለመላቸውና ዝንባሌዎቻቸው እንደ ተከተሉ ክፍሎች ነውን?

ከሙሐመድ ምዕራፍ (13) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከመካ ወተው ወደ መዲና ለመሄድ ወደ ዋሻው እየሄዱ እያሉ ዘወር ብለው መካን በማየት አንቺ ከሀገሮች ሁሉ አላህ ዘንድ የተወደድሽ ነሽ እኔም ዘንድ እንዲሁ ጣዖት አምላኪዎች ባያበርሩኝ ኖሮ ከአንቺ መውጣ አልፈልግም ነበር በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ጦበሪ፤ ሱዩጢ፤ ኢብኑ አቢሀቲም)

مَّثَلُ ٱلْجَنَّةِ ٱلَّتِي وُعِدَ ٱلْمُتَّقُونَ ۖ فِيهَآ أَنْهَٰرٌ مِّن مَّآءٍ غَيْرِ ءَاسِنٍ وَأَنْهَٰرٌ مِّن لَّبَنٍ لَّمْ يَتَغَيَّرْ طَعْمُهُۥ وَأَنْهَٰرٌ مِّنْ خَمْرٍ لَّذَّةٍ لِّلشَّٰرِبِينَ وَأَنْهَٰرٌ مِّنْ عَسَلٍ مُّصَفًّى ۖ وَلَهُمْ فِيهَا مِن كُلِّ ٱلثَّمَرَٰتِ وَمَغْفِرَةٌ مِّن رَّبِّهِمْ ۖ كَمَنْ هُوَ خَٰلِدٌ فِى ٱلنَّارِ وَسُقُوا۟ مَآءً حَمِيمًا فَقَطَّعَ أَمْعَآءَهُمْ ﴿١٥﴾

**15.** ያች አላህን ለሚፈሩ ሰዎች ቃል የተገባችው ገነት (ይህን ትመስላለች)፤ በውስጧ ሽታው ከማይለወጥ ውሃ የሆኑ ወንዞች፤ ጣዕሙ የማይለወጥ ወተት የሆኑ ወንዞች፤ ለጠጪዎች እጅግ ጣፋጭ የሆኑ የወይን ጠጅ ወንዞችና የንፁህ ማር ወንዞች አሉባት። ከውስጧ ሁሉም የፍራፍሬ አይነቶች ተዘጋጅተውላቸዋል። እነኚህ መንገዶች እንደነዚያ እሳት ውስጥ ዘወትር እንደሚኖሩ የፈላ ውሃም እንዲጠጡ እንደሚደረጉትና ውሃውም የሆድ ዕቃቸውን እንደሚበጣጥስባቸው ናቸውን?

وَمِنْهُم مَّن يَسْتَمِعُ إِلَيْكَ حَتَّىٰٓ إِذَا خَرَجُوا۟ مِنْ عِندِكَ قَالُوا۟ لِلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْعِلْمَ مَاذَا قَالَ ءَانِفًا ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ طَبَعَ ٱللَّهُ عَلَىٰ قُلُوبِهِمْ وَٱتَّبَعُوٓا۟ أَهْوَآءَهُمْ ﴿١٦﴾

**16.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከእነርሱ መካከል ወደ አንተ የሚያዳምጡ አሉ። ከአንተ ዘንድ በወጡ ጊዜ ለእነዚያ እውቀት ለተሰጡት አሁን ምን አለ? ይላሉ። እነዚያ እነዚህ በልቦቻቸው ላይ አላህ ያተማቸው ዝንባሌዎቻቸውን የተከተሉ ናቸው።

ከሙሐመድ ምዕራፍ (16) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩ (ﷺ) አጠገብ ሙስሊሞችና አስመሳዮች በአንድ ተቀምጠው ሲያዳምጡ ሙዕሚኖች በትክክል ሰምተውና ተረድተው ሲወጡ አስመሳዮች ግን በትክክል ስለማያዳምጡ ሲወጡ ስለሚጠፋቸው ሙዕሚኖችን ቀደም ሲል ሙሐመድ ምን አለ እያሉ ይጠይቋቸው ስለነበረ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَٱلَّذِينَ ٱهْتَدَوْا۟ زَادَهُمْ هُدًى وَءَاتَىٰهُمْ تَقْوَىٰهُمْ ﴿١٧﴾

**17.** እነዚያ ወደ ቀናው መንገድ የተመሩት አላህ መመራትን ጨመረላቸው። ከእሳት መጠበቂያዎችንም ሰጣቸው።

فَهَلْ يَنظُرُونَ إِلَّا ٱلسَّاعَةَ أَن تَأْتِيَهُم بَغْتَةً ۖ فَقَدْ جَآءَ أَشْرَاطُهَا ۚ فَأَنَّىٰ لَهُمْ إِذَا جَآءَتْهُمْ ذِكْرَىٰهُمْ ﴿١٨﴾

**18.** የሰዓቲቱን በድንገት መምጣት እንጂ ሌላን ይጠባበቃሉን? ምልክቶቿም በእርግጥ መጥተዋል። በመጣባቸውም ጊዜ ማስታወሻቸው ለእነርሱ እንዴት ይጠቅማቸዋል።

فَٱعۡلَمۡ أَنَّهُۥ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا ٱللَّهُ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لِذَنۢبِكَ وَلِلۡمُؤۡمِنِينَ وَٱلۡمُؤۡمِنَٰتِۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ مُتَقَلَّبَكُمۡ وَمَثۡوَىٰكُمۡ ١٩

**19.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነሆ ከአላህ ሌላ ትክክለኛ አምላክ አለመኖሩንም እወቅ። ስለ ስህተትህም ሆነ ለወንድ ለሴት ምዕመናን ስህተት ምህረትን ለምን። አላህ መዘዋወሪያችሁንም ሆነ መርጊያችሁን ያውቃል።

**ከነብዩ ሙሐመድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-19) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

1. ትርፋማው መንገድና ለኪሳራ የሚያበቃው መንገድ የቱ የቱ እንደሆነ ማስተማር፤
2. የትኛውም ኸይር ስራ ከሽርክና ከክህደት ጋር ከሆነ ምንም አይነት ጥቅም እንደሌለው፤
3. በትምህርት ላይ ምሳሌዎችን መጥቀስ ከፍተኛ ጥቅም እንዳለው፤
4. የጅሃድ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉ በየ አንዳንዱ ግዴታ መሆኑን፤
5. ጂሃድ ውስጥ ለሚማረኩ ሰዎችን በተመለከተ መሪው በነፃ በመልቀቅና ገንዘብ ተቀብሎ በመልቀቅ ላይ ምርጫ እንዳለው።
6. ለአላህ ዲን ሲሉም መስዋዕት የከፈሉ ሰዎች ከፍተኛ ማዕረግ እንዳላቸው፤
7. የአላህን ዲን የረዳ ሰው ሁሉ ትክክለኛ ድል እንደሚታደል፤ ከሓዲያን እንኳንስ በአኼራ በዚህ ዓለምም ቢሆን ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል ማስጠንቀቅ፤
8. አዋቂ ማለት በሌላ የተመከረ መሆኑን፤
9. አላህ የፈርሃዊያን ልዩ ወዳጅ እንደሆነ፤
10. በእምነታቸው ላይ ፅናት ያላቸውና ማቴሪያሊስቶችን አበጥሮ መለየት፤
11. ነብዩ (ﷺ) ከከሓዲያን በሚሰነዘርባቸው አስቀያሚ ነገሮች እንዳሰማቸው ማፅናናት፤
12. ጀነትን ለመውረስ አላህን መፍራት ትልቅ ምክንያት እንደሆነ፤
13. ከጀነት ፀጋዎች አልፎ አልፎ ማውሳት፤
14. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥና እድለኝነትና እድለቢስነት ፈፅሞ እንደማይወዳደሩ።
15. የራስ ስሜትን መከተል ከፍተኛ አደጋ እንዳለው፤
16. ከአላህ ሌላ አምላክ የሌለ መሆኑን እንማራለን።

وَيَقُولُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَوۡلَا نُزِّلَتۡ سُورَةٞۖ فَإِذَآ أُنزِلَتۡ سُورَةٞ مُّحۡكَمَةٞ وَذُكِرَ فِيهَا ٱلۡقِتَالُ رَأَيۡتَ ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٞ يَنظُرُونَ إِلَيۡكَ نَظَرَ ٱلۡمَغۡشِيِّ عَلَيۡهِ مِنَ ٱلۡمَوۡتِۖ فَأَوۡلَىٰ لَهُمۡ ٢٠

**20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ ያመኑት ሰዎች ለዲን ለመታገል ግፊት ያለበት የቁርአን ምእራፍ አይወረድም ኖሯልን? ይላሉ። የጠነከረም ምእራፍ በወረደና በውስጡም መጋደል በተወሰነ ጊዜ እነዚያን በልቦቻቸው ውስጥ የንፍቅና በሽታ ያለባቸውን ሰዎች ከሞት የሆነ መከራ በእርሱ ላይ እንደወደቀበት ሰው አስተያየት ወደ አንተ ሲመለከቱ ታያቸዋለህ። ለእነርሱም ወዮላቸው።

طَاعَةٌ وَقَوْلٌ مَّعْرُوفٌ فَإِذَا عَزَمَ ٱلْأَمْرُ فَلَوْ صَدَقُوا۟ ٱللَّهَ لَكَانَ خَيْرًا لَّهُمْ ﴿٢١﴾

**21.** ታዛዥነትና መልካም ንግግር ይሻላቸዋል። ትዕዛዙም ቁርጥ በሆነ ጊዜ ለአላህ ትእዛዝ እውነተኞች በሆኑ ኖሮ ለእነርሱ የተሻለ በሆነ ነበር።

فَهَلْ عَسَيْتُمْ إِن تَوَلَّيْتُمْ أَن تُفْسِدُوا۟ فِى ٱلْأَرْضِ وَتُقَطِّعُوٓا۟ أَرْحَامَكُمْ ﴿٢٢﴾ أُو۟لَـٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ لَعَنَهُمُ ٱللَّهُ فَأَصَمَّهُمْ وَأَعْمَىٰٓ أَبْصَـٰرَهُمْ ﴿٢٣﴾ أَفَلَا يَتَدَبَّرُونَ ٱلْقُرْءَانَ أَمْ عَلَىٰ قُلُوبٍ أَقْفَالُهَآ ﴿٢٤﴾

**22-24.** ብትሾሙም በምድር ላይ ማበላሸትን ዝምድናችሁንም* መቁረጥን ከጀላችሁን? እነዚያ አላህ የረገማቸው ያደነቁራቸውም ዓይኖቻቸውንም ያወራቸው ማለት ናቸው። ቁርኣንን አያስተነትኑምን? በእውነቱ በልቦቻቸው ላይ ቁልፎች አሉባቸውን?።

✶ የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ፍጡራንን ፈጥሮ ሲጨርስ ነፍስ ተነሳችና አላህን ያዘች። አላህም «ምንድን ነው ነገሩ» አላት። እሷም «እኔ ዝምድናን ከሚቆርጥ ባንተ እጠበቃለሁ» አለችው። እሱም «የቆረጠሽን እንድቆርጠው፤ የቀጠለሽን እንድቀጥለው አትወጂምን?» አላት። አቡ ሁረይራህ ከፈለጋችሁ «ብትሾሙም በምድር ላይ ማበላሸትን ዝምድናችሁንም መቁረጥ ከጀላችሁን?» (ሙሐመድ 22) የሚለውን አንብቡ» አሉ»

إِنَّ ٱلَّذِينَ ٱرْتَدُّوا۟ عَلَىٰٓ أَدْبَـٰرِهِم مِّنۢ بَعْدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمُ ٱلْهُدَى ٱلشَّيْطَـٰنُ سَوَّلَ لَهُمْ وَأَمْلَىٰ لَهُمْ ﴿٢٥﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَالُوا۟ لِلَّذِينَ كَرِهُوا۟ مَا نَزَّلَ ٱللَّهُ سَنُطِيعُكُمْ فِى بَعْضِ ٱلْأَمْرِ ۖ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ إِسْرَارَهُمْ ﴿٢٦﴾

**25-26.** እነዚያ ቅኑው መንገድ ከተብራራላቸው በኋላ ወደ ኋላቸው የተመለሱት ሰይጣን ለእነርሱ መመለሻቸውን ሸለመላቸው። ለእነርሱም አዘናጋቸው። ይህ እነርሱ ለእነዚያ አላህ ያወረደውን ለጠሉት በነገሩ ከፊሉን እንታዘዛችኋለን ያሉ በመሆናቸው ነው። አላህም መደበቂያቸውንም ያውቃል።

فَكَيْفَ إِذَا تَوَفَّتْهُمُ ٱلْمَلَـٰٓئِكَةُ يَضْرِبُونَ وُجُوهَهُمْ وَأَدْبَـٰرَهُمْ ﴿٢٧﴾ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمُ ٱتَّبَعُوا۟ مَآ أَسْخَطَ ٱللَّهَ وَكَرِهُوا۟ رِضْوَٰنَهُۥ فَأَحْبَطَ أَعْمَـٰلَهُمْ ﴿٢٨﴾

**27-28.** መላዕክት ፊቶቻቸውንና ጀርባዎቻቸውን የሚመቱ ሲሆኑ በገደሏቸው ጊዜ (ሁኔታቸው እንዴት ይሆናል?) ይህ እነርሱ አላህን ያስቆጣውን ነገር ሁሉ ስለተከተሉ ውዴታውንም ስለጠሉ ነው። ስለዚህ ስራዎቻቸውን አበላሸባቸው።

**ከሙሐመድ ምዕራፉ ከአንቀፅ (20-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ኸይርን መመኘት ተገቢ መሆኑን፤
2. ከቁርኣን ውስጥ የተሻረና ያልተሻረ እንዳለው ሁሉም የአላህ ቃል መሆኑን፤
3. መንፈስ ደካማነት ፈሪነትን ማውገዝ፤
4. ሁል ጊዜም ኸይርን መመኘት ተገቢ መሆኑን፤
5. ከቁርኣን ውስጥ የተሻረና ያልተሻረ እንዳለው ሁሉም የአላህ ቃል መሆኑን፤
6. መንፈስ ደካማነት ፈሪነትን ማውገዝ፤
7. ከሰዎች ሁሉ መጥፎ ማለት ሲሾም በሸርክና በታላላቅ ወንጀሎች የሚዘፍቅ መሆኑን፤
8. ቁርኣንን ሲያነቡም ሆነ ሲያዳምጡ ስርአቱን ጠብቆ መሆን እንዳለበት፤
9. ወደ ወንጀል መዞርም ሆነ ከኢስላም መውጣት ዋናው ምክንያት ሰይጣን ማስዋቡ መሆኑ፤
10. ኢስላምን ለማጥፋት (ለማዳከም) በሚደረግ ሂደቶች ትብብር ማድረግ ከረዳ ኢስላምን ከመቀየር አንዱ መሆኑን፤
11. የቀብር ቅጣት ያለና ሊካድ የማይችል መሆኑን እንማራለን።

أَمۡ حَسِبَ ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٌ أَن لَّن يُخۡرِجَ ٱللَّهُ أَضۡغَٰنَهُمۡ ﴿٢٩﴾ وَلَوۡ نَشَآءُ لَأَرَيۡنَٰكَهُمۡ
فَلَعَرَفۡتَهُم بِسِيمَٰهُمۡۚ وَلَتَعۡرِفَنَّهُمۡ فِي لَحۡنِ ٱلۡقَوۡلِۚ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ أَعۡمَٰلَكُمۡ ﴿٣٠﴾

**29-30.** እነዚያ በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው ሰዎች አላህ በሙስሊሞች ላይ የነበራቸዉን ቂሞቻቸውን አለማውጣቱን ጠረጠሩን? (ሙሐመድ ሆይ)፣ ብንፈልግ ኖሮ እነርሱን ባሳየንህና በምልክታቸውም በእርግጥ በአወካቸው ነበር። ንግግርንም በማሸሞራቸው በእርግጥ ታውቃቸዋለህ። አላህ ስራዎቻችሁን ያውቃል።

وَلَنَبۡلُوَنَّكُمۡ حَتَّىٰ نَعۡلَمَ ٱلۡمُجَٰهِدِينَ مِنكُمۡ وَٱلصَّٰبِرِينَ وَنَبۡلُوَاْ أَخۡبَارَكُمۡ ﴿٣١﴾

**31.** (አማኞች ሆይ)፣ ከናንተ መካከል ተዋጊዎችንና ታጋሾቹን እስከምንገልፅ ድረስ በእርግጥ እንሞክራችኋለን። ወሪዎቻችሁንም እንሞክራችኋለን።*

* አንድ ከቀደምት ምሁራን መካከል ይህ አንቀፅ አንብበው ከሞከርከንማ አለቅን ማለት ነው እያሉ እየደጋገሙ ሙሉ ሌሊት ያደሩ ዐሊም ታሪክ ይነገራል።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ وَشَآقُّواْ ٱلرَّسُولَ مِنۢ بَعۡدِ مَا تَبَيَّنَ لَهُمُ ٱلۡهُدَىٰ
لَن يَضُرُّواْ ٱللَّهَ شَيۡـٔٗا وَسَيُحۡبِطُ أَعۡمَٰلَهُمۡ ﴿٣٢﴾

**32.** እነዚያ በአላህ የካዱና ከአላህም መንገድ ሰዎችን ያገዱ ለእነርሱም ቅኑ መንገድ ከተገለፀላቸው በኋላ መልዕክተኛውን የተከራከሩ ሁሉ አላህን በምንም አይጎዱትም። ስራዎቻቸውንም በእርግጥ ያበላሻል።

۞ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ أَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَ وَلَا تُبۡطِلُوٓاْ أَعۡمَٰلَكُمۡ ٣٣

**33.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህን ተገዙ መልዕክተኛውንም ታዘዙ። ስራዎቻችሁንም አታበላሹ።*

✶ ከዚህ የቁርኣን አባባል በበጎ ፍቃደኝነት የሚጀመር ኸይር ተግባር ሁሉ መቋረጥ እንደሌለበት ከተቋረጠም ቀዷ ማውጣት ግዴታ ይሆናል ብለዋል።

ከሙሐመድ ምዕራፍ (33) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አብደላህ ኢብኑ ዑመር እንደሚሉት እኛ የነብዩን (ﷺ) ባልደረቦች ከላኢላሀ ኢለሏህ ጋር ምንም አይነት ወንጀል አይጎዳም። ከሽርክ ጋርም መልካም ስራ እንደማይጠቅም ሁሉ እንል ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ይህ አንቀፅ በወረደ ጊዜ ግን ስራ የሚያበላሹ ነገሮች ምን ምን ናቸው ብለን ተጠያየቅንና ታላላቅ ወንጀሎችና ዝሙት ናቸው ብለን ደመደምን ከዚያም ከነዚህ ታላላቅ ወንጀሎችን የፈፀመ ሰው ስናይ ይህ ሰው አለቀለት ብለን እንወስንበት ነበር ከዚያም አላህ በእርሱ ማጋራትን ፈፅሞ አይምርም። ከዚህ ሌላ ያለውን ኃጢአት ግን ለሚሻው ሰው ይምራል። በአላህ የሚያጋራ ሰው ታላቅን ኃጢአት በእርግጥ ፈፀመ። (አንኒሳእ፡ 48) የሚለው ቁርኣን ወርዶ ከሽርክ በታች ያለ ወንጀል ሊያስቀጣ ቢችልም ሊማር እንደሚችል ተስፋ በመስጠቱ ተስፋ ማድረግ ጀመርን ብለዋል። (ኢብኑ ጀሪር፤ መርደወይና ሱዩጢ)።

إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ ثُمَّ مَاتُواْ وَهُمۡ كُفَّارٞ فَلَن يَغۡفِرَ ٱللَّهُ لَهُمۡ ٣٤

**34.** እነዚያ በአላህ የካዱ ከአላህ መንገድ ሌሎችን ያገዱና ከዚያ እነርሱ ከሓዲያን ሆነው የሞቱ አላህ ለእነርሱ በፍፁም አይምርም።

فَلَا تَهِنُواْ وَتَدۡعُوٓاْ إِلَى ٱلسَّلۡمِ وَأَنتُمُ ٱلۡأَعۡلَوۡنَ
وَٱللَّهُ مَعَكُمۡ وَلَن يَتِرَكُمۡ أَعۡمَٰلَكُمۡ ٣٥

**35.** እናንተ አሸናፊዎች ስትሆኑና አላህ ከናንተ ጋር ሲሆን አትድከሙ። ወደ እርቅም አትጥሩ። ስራዎቻችሁን ፈፅሙ አያጎድልባችሁም።

إِنَّمَا ٱلۡحَيَوٰةُ ٱلدُّنۡيَا لَعِبٞ وَلَهۡوٞۚ وَإِن تُؤۡمِنُواْ وَتَتَّقُواْ يُؤۡتِكُمۡ أُجُورَكُمۡ وَلَا يَسۡـَٔلۡكُمۡ
أَمۡوَٰلَكُمۡ ٣٦ إِن يَسۡـَٔلۡكُمُوهَا فَيُحۡفِكُمۡ تَبۡخَلُواْ وَيُخۡرِجۡ أَضۡغَٰنَكُمۡ ٣٧

**36-37.** ቅርቢቱ ሕይወት ጫወታና ዛዛታ ብቻ ናት። በአላህ ብታምኑም ቅጣቱን ብትጠነቀቁም ምንዳዎቻችሁን ይሰጣችኋል። ገንዘቦቻችሁንም ሁሉ አይጠይቃችሁም። እርሷን ቢጠይቃችሁና ችክ ቢልባችሁ ትሰስታላችሁ። ቂሞቻችሁንም ያወጣል።

هَٰٓأَنتُمۡ هَٰٓؤُلَآءِ تُدۡعَوۡنَ لِتُنفِقُواْ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ فَمِنكُم مَّن يَبۡخَلُۖ
وَمَن يَبۡخَلۡ فَإِنَّمَا يَبۡخَلُ عَن نَّفۡسِهِۦۚ وَٱللَّهُ ٱلۡغَنِيُّ وَأَنتُمُ ٱلۡفُقَرَآءُۚ وَإِن تَتَوَلَّوۡاْ
يَسۡتَبۡدِلۡ قَوۡمًا غَيۡرَكُمۡ ثُمَّ لَا يَكُونُوٓاْ أَمۡثَٰلَكُم ٣٨

38. (አማኞች ሆይ)፣ አስተውሉ። እናንተ እነዚያ በአላህ መንገድ ትለግሱ ዘንድ የምትጥጠሩ ናችሁ። ከናንተም መካከልም የሚሰስት ሰው አለ። የሚሰስት ሰው የሚሰስተው በራሱ ላይ ብቻ ነው። አላህ በራሱ ተብቃቂ ነው። እናንተ ግን ድሆች ናችሁ። ብትሸሹም ሌሎችን ህዝቦች በቦታችሁ ይለውጣል። ከዚያ በአላህ ባለመታዘዝ እንደናንተ ብጤዎቻችሁ አይሆኑም።

**ከሙሐመድ ምዕራፍ ከአንቀፅ (29-38) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. አንድ ነገር የወደደ ሰው በፊቱም ላይ ሆነ በአንደበቱ ላይ ይታወቃል፤
2. ወደ ኢስላም የገባ ሰው በህይወቱም ሆነ በንብረቱ መፈተኑ የማይቀር መሆኑን፤
3. የከሃዲና የሙሽሪከን ተግባራት ውድቅ መሆኑን።
4. የአላህና የመልዕክተኛን ትዕዛዝ ማክበር ግዴታ መሆኑን፤
5. ኸይር ስራን ለመስራት የጀመረ ሰው መጨረስ ግዴታ መሆኑን፤
6. ኸይር ስራዎች በይዩልኝ ወይም ከኢስላም በመውጣት እንደሚበላሹ፤
7. ጠላትን በጉልበት ማንበርከክ የተቻለ ከእነሱ ጋር ለመታረቅ መለማመጥ ክልክል መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (48)
# አገር የመክፈት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ፈትህ)

سُورَةُ الفَتْحِ

### የወረደው በመዲና ነው። የአናቅፁ ብዛት (29) ናቸው።
### የሱረቱ አል ፈትሕ መግቢያ

ያአላህ ፈቃዱ ሆኖ ነብዩን በቀላሉ ወደ መካ እንዲገቡ ያመቻቸለትን በእሱም ምክንያት ኢስላምን በማስፋፋት ሙስሊሞችን በማጠናከር አስመሳዮች ከሓዲያን አላህ መልዕክተኛውን ነብዩን (ﷺ) ሊረዳ አይችልም በማለታቸው እየጠበቃቸው ያለውን ቅጣት አላህ ነብዩን አብሳሪና አስፈራሪ አድርጎ በመቀጠል የእውነት አማኞች እነማን እንደሆኑ የቃል ኪዳኗን ታሪክ በመጥቀስ ያብራራና ከነብዩ (ﷺ) ጋር ዘመቻ ለመውጣት ልዩ ልዩ ምክንያቶችን የሚያቀርቡትን አስመሳዮች ቅጥፈት ያጋልጣል። በመቀጠል ሙዕሚኖች ሀይለኛ ሰዎች እንዲዋጉ ጥሪ እንዲደረግላቸው በትክክለኛ ምክንያት መቅረትም ችግር እንደሌለው ይተነትንና የቃል ኪዳን ሰዎች አላህ እንደወደደላቸው፤ ከህዲዎች አማኞች ጋር ጦርነት ሊከፍቱ እንደሚሹ ያሳውቅና ከሓዲያንን ከአማኞች; አማኞችን ከከሓዲያን; መካን የከፈቱለት እንዳይጎዳዱ ማገዱ ለምን እንደሆነ ጠቅሞ ነብዩ ያዩት መናም ትክክለኛ እንደሆነ በይፋ ያበስራል።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንደሚሉት ከሁደይቢያ ዘመቻ ከመካ በመከልከላችን በሐዘን ስንመለስ ይህ ምዕራፍአወረደልን። በዚህ ጊዜ ነብዩ ዛሪ ከዱንያ ደስታዎች በጠቅላላ የተሸለ ምራፍ ወረደልኝ በማለት አበሰሩን። ብለዋል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِنَّا فَتَحۡنَا لَكَ فَتۡحٗا مُّبِينٗا ١ لِّيَغۡفِرَ لَكَ ٱللَّهُ مَا تَقَدَّمَ مِن ذَنۢبِكَ وَمَا تَأَخَّرَ وَيُتِمَّ
نِعۡمَتَهُۥ عَلَيۡكَ وَيَهۡدِيَكَ صِرَٰطٗا مُّسۡتَقِيمٗا ٢ وَيَنصُرَكَ ٱللَّهُ نَصۡرًا عَزِيزًا ٣

**1-3.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ለአንተ ግልፅ የሆነን ድል (መካን) በመክፈት ለገስንህ። አላህ የአለፈውንና የሚመጣውን* ኃጢአትክን ሊምር ፀጋውንም በአንተ ላይ ሊሞላ ቀጥተተኛውንም መንገድ ሊመራ (መካን ከፈተልህ)። አላህ ብርቱን እርዳታ ሊረዳህ (መካን ከፈተልህ)።

✷ የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አልሙጊራህ እንዳስተላፉት እግሮቻቸውን እስከሚያደነዝዙ ድረስ የለሊትን ሶላት ቆመው ይሰግዱ ነበር። ከሰዎች መካከልም፦ «አላህ የርስዎን የቀድሞና የወደፊት ኃጢያትዎን ሰርዞሎታል አይደለምን?» ሲል ጠየቃቸው። እሳቸውም «አላህን አመስጋኝ አልሆንምን?» አሉ።

هُوَ ٱلَّذِىٓ أَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ فِى قُلُوبِ ٱلْمُؤْمِنِينَ لِيَزْدَادُوٓا۟ إِيمَـٰنًا مَّعَ إِيمَـٰنِهِمْ ۗ وَلِلَّهِ جُنُودُ
ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلِيمًا حَكِيمًا ﴿٤﴾

4. እርሱ (አላህ) ያ በምዕመናን ልቦች ውስጥ ከእምነታቸው ጋር እምነትን ይጨምሩ ዘንድ እርጋታን* ያወረደ ነው፡፡ አላህ የሰማይና የምድር ሰራዊት ሁሉ የሱ ብቻ ነው፡፡ አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው፡፡

* ትዕግስትን፤ በአላህ መተማመን ሊሆን ይችላል ተፈስሯል፡፡

لِّيُدْخِلَ ٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَـٰتِ جَنَّـٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ خَـٰلِدِينَ فِيهَا وَيُكَفِّرَ
عَنْهُمْ سَيِّـَٔاتِهِمْ ۚ وَكَانَ ذَٰلِكَ عِندَ ٱللَّهِ فَوْزًا عَظِيمًا ﴿٥﴾

5. ወንድ ምዕመናንና ሴት ምዕመናትን በስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘወታሪዎች ሲሆኑ ሊያስገባቸው ከነርሱም ኃጢአቶቻቸውን ሊያብስላቸው (መካን ከፈተልህ)፡፡ ይህም ከአላህ ዘንድ የሆነ ታላቅ መታደል ነው፡፡

አገር የመክፈት (5) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሶሃቦች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው እንኳን ደስ አለዎት ለእኛስ ምን አለን ብለው ሲጠይቋቸው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡

وَيُعَذِّبَ ٱلْمُنَـٰفِقِينَ وَٱلْمُنَـٰفِقَـٰتِ وَٱلْمُشْرِكِينَ وَٱلْمُشْرِكَـٰتِ ٱلظَّآنِّينَ بِٱللَّهِ ظَنَّ ٱلسَّوْءِ ۚ
عَلَيْهِمْ دَآئِرَةُ ٱلسَّوْءِ ۖ وَغَضِبَ ٱللَّهُ عَلَيْهِمْ وَلَعَنَهُمْ وَأَعَدَّ لَهُمْ جَهَنَّمَ ۖ وَسَآءَتْ مَصِيرًا ﴿٦﴾

6. በአላህም ክፉ ጥርጣሬን ተጣራጣሪዎቹን መናፍቃንንና መናፍቃትን ወንዶች አጋሪዎችና ሴቶች አአጋሪዎችን ያሰቃይ ዘንድ (በትግል አዘዘ)፡፡ በእነርሱ ላይ ክፉ ከባቢ አለባቸው፡፡ በእነርሱ ላይ አላህ ተቆጣባቸው ረገማቸውም፡፡ ለእነርሱ ገሀነምን አዘጋጀላቸው መመለሻነቷም ከፋች፡፡

وَلِلَّهِ جُنُودُ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿٧﴾

7. ለአላህ የሰማያትና የምድር ሰራዊቶች አሉት፡፡ አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነው፡፡

إِنَّآ أَرْسَلْنَـٰكَ شَـٰهِدًا وَمُبَشِّرًا وَنَذِيرًا ﴿٨﴾ لِّتُؤْمِنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَتُعَزِّرُوهُ وَتُوَقِّرُوهُ ۚ
وَتُسَبِّحُوهُ بُكْرَةً وَأَصِيلًا ﴿٩﴾

8-9. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ መስካሪ፤ አብሳሪና አስፈራሪ አድርገን በእርግጥ ላክንህ፡፡ በአላህ ልታምኑ በመልዕክተኛውም ልታምኑ፤ ልትረዱትና ልታከብሩት፤ አላህን በጠዋትና ከቀትር በኋላ ልታወድሱትም (ላክንህ)፡፡

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُبَايِعُونَكَ إِنَّمَا يُبَايِعُونَ ٱللَّهَ يَدُ ٱللَّهِ فَوْقَ أَيْدِيهِمْ ۚ فَمَن نَّكَثَ فَإِنَّمَا يَنكُثُ عَلَىٰ نَفْسِهِۦ ۖ وَمَنْ أَوْفَىٰ بِمَا عَٰهَدَ عَلَيْهُ ٱللَّهَ فَسَيُؤْتِيهِ أَجْرًا عَظِيمًا ﴿١٠﴾

**10.** እነዚያ ቃል ኪዳን የሚጋቡ ቃል ኪዳን የሚጋቡት አላህን ብቻ ነው። የአላህ እጅ ከእጆቻቸው በላይ ነው። ያፈረሰም ሰው የሚፈርሰው በነፍሱ ላይ ብቻ ነው። በእርሱ ላይ አላህን ቃል ኪዳን የተጋባበትን የሞላ ሰው ታላቅ ምንዳ በእርግጥ ይሰጠዋል።

سَيَقُولُ لَكَ ٱلْمُخَلَّفُونَ مِنَ ٱلْأَعْرَابِ شَغَلَتْنَآ أَمْوَٰلُنَا وَأَهْلُونَا فَٱسْتَغْفِرْ لَنَا ۚ يَقُولُونَ بِأَلْسِنَتِهِم مَّا لَيْسَ فِى قُلُوبِهِمْ ۚ قُلْ فَمَن يَمْلِكُ لَكُم مِّنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔا إِنْ أَرَادَ بِكُمْ ضَرًّا أَوْ أَرَادَ بِكُمْ نَفْعًۢا ۚ بَلْ كَانَ ٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرًۢا ﴿١١﴾

**11.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአዕራብ ሰዎች (ከአረብ አርብቶ አደሮች) እነዚያ ከዘመቻ ወደ ኋላ የቀሩት ላንተ ገንዘቦቻችንና ቤሰተቦቻችን አስቸገሩን ስለዚህ ምህረትን ለምንልን ይሉሃል። በልቦቻቸው ውስጥ የሌለውን ነገር በምላሶቻቸው ይናገራሉ። አላህ እናንተን መጉዳትም ሆነ መጥቀም ቢፈልግ ከአላህ ለእናተ አንዳችን ለመከላከል የሚችል ማን ነው? በእውነቱ አላህ ለምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው በላቸው።

بَلْ ظَنَنتُمْ أَن لَّن يَنقَلِبَ ٱلرَّسُولُ وَٱلْمُؤْمِنُونَ إِلَىٰٓ أَهْلِيهِمْ أَبَدًا وَزُيِّنَ ذَٰلِكَ فِى قُلُوبِكُمْ وَظَنَنتُمْ ظَنَّ ٱلسَّوْءِ وَكُنتُمْ قَوْمًۢا بُورًا ﴿١٢﴾ وَمَن لَّمْ يُؤْمِنۢ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ فَإِنَّآ أَعْتَدْنَا لِلْكَٰفِرِينَ سَعِيرًا ﴿١٣﴾

**12-13.** ይልቁንም መልዕክተኛው እና ምዕመናኖቹ ወደ የቤተሰቦቻቸው ፈፅሞ ባለመመለሳቸው ጠረጠራችሁ። ይህም በልቦቻችሁ ውስጥ ተሸለመላችሁ። መጥፎንም መጠርጠር ጠረጠራችሁ ጠፊዎች ህዝቦችም ሆናችሁ። በአላህና በመልዕክተኛው ያለመነ ሰው እኛ ለከሐዲያን እሳትን አዘጋጅተናል።

وَلِلَّهِ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ يَغْفِرُ لِمَن يَشَآءُ وَيُعَذِّبُ مَن يَشَآءُ ۚ وَكَانَ ٱللَّهُ غَفُورًا رَّحِيمًا ﴿١٤﴾

**14.** የሰማያትና የምድር ንግስና የአላህ ብቻ ነው። ለሚፈልገው ሰው ወደ ቀናው ይምራል። የሚፈልገውንም ሰው ይቀጣል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

سَيَقُولُ ٱلْمُخَلَّفُونَ إِذَا ٱنطَلَقْتُمْ إِلَىٰ مَغَانِمَ لِتَأْخُذُوهَا ذَرُونَا نَتَّبِعْكُمْ ۖ يُرِيدُونَ أَن يُبَدِّلُوا۟
كَلَـٰمَ ٱللَّهِ ۚ قُل لَّن تَتَّبِعُونَا كَذَٰلِكُمْ قَالَ ٱللَّهُ مِن قَبْلُ ۖ فَسَيَقُولُونَ بَلْ تَحْسُدُونَنَا ۚ بَلْ كَانُوا۟
لَا يَفْقَهُونَ إِلَّا قَلِيلًا ﴿١٥﴾ قُل لِّلْمُخَلَّفِينَ مِنَ ٱلْأَعْرَابِ سَتُدْعَوْنَ إِلَىٰ قَوْمٍ أُو۟لِى بَأْسٍ
شَدِيدٍ تُقَـٰتِلُونَهُمْ أَوْ يُسْلِمُونَ ۖ فَإِن تُطِيعُوا۟ يُؤْتِكُمُ ٱللَّهُ أَجْرًا حَسَنًا ۖ وَإِن تَتَوَلَّوْا۟ كَمَا
تَوَلَّيْتُم مِّن قَبْلُ يُعَذِّبْكُمْ عَذَابًا أَلِيمًا ﴿١٦﴾

**15-16.** ከጠላት የተማረኩትን ገንዘቦች ልትይዙ በሄዳችሁ ጊዜ እነዚያ ወደ ኋላ የቀሩት ሰዎች ተውን እንከተላችሁ ይሏችኋል። በዚህም የአላህን ቃል ሊለውጡ ይፈልጋሉ። ፈፅሞ አትከተሉንም ልክ እንደዚሃችሁ ቃል የመሰለ ከዚህ በፊት አላህም ብሏል በሏቸው። ይልቁንም ትመቀኙናላችሁ ይላሉም። በእውነት እነርሱም ጥቂትን እንጂ የማያውቁ ነበሩ። ከአዕራቦች ወደ ኋላ ለቀሩት በላቸው የብርቱ ጭካኔ ባለቤት ወደ ሆኑ ህዝቦች ውጊያ ወደ ፊት ትጠራላችሁ ትጋደሏቸዋላችሁ። ወይም ይሰልማሉ ብትታዘዙም አላህ መልካም ምንዳን ይሰጣችኋል። ከአሁን በፊት እንደ ሸሻችሁ። ብትሸሹም አሳማሚ ቅጣት ይቀጧችኋል።

لَّيْسَ عَلَى ٱلْأَعْمَىٰ حَرَجٌ وَلَا عَلَى ٱلْأَعْرَجِ حَرَجٌ وَلَا عَلَى ٱلْمَرِيضِ حَرَجٌ ۗ وَمَن يُطِعِ ٱللَّهَ
وَرَسُولَهُۥ يُدْخِلْهُ جَنَّـٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَـٰرُ ۖ وَمَن يَتَوَلَّ يُعَذِّبْهُ عَذَابًا أَلِيمًا ﴿١٧﴾

**17.** (ሰዎች ሆይ!) በአይነስውር ላይ (ከዘመቻ በመቅረቱ) ኃጢአት የለበትም። በአንካሳም ላይ ኃጢአት የለበትም በበሽተኛም ላይ ኃጢአት የለበትም። አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ሁሉ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያስገባዋል። የሚፈልገውንም ሰው አሳማሚ ቅጣት ይቀጣዋል።

۞ لَّقَدْ رَضِىَ ٱللَّهُ عَنِ ٱلْمُؤْمِنِينَ إِذْ يُبَايِعُونَكَ تَحْتَ ٱلشَّجَرَةِ فَعَلِمَ مَا فِى قُلُوبِهِمْ فَأَنزَلَ ٱلسَّكِينَةَ
عَلَيْهِمْ وَأَثَـٰبَهُمْ فَتْحًا قَرِيبًا ﴿١٨﴾ وَمَغَانِمَ كَثِيرَةً يَأْخُذُونَهَا ۗ وَكَانَ ٱللَّهُ عَزِيزًا حَكِيمًا ﴿١٩﴾

**18-19.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከምዕመናኖቹ በዛፏቱ ስር ቃል ኪዳን በሚጋቡህ ጊዜ አላህ በእርግጥ ስራቸዉን ወደደላቸው። በልቦቻቸውም ውስጥ ያለውን ዐወቀ። በነሱም ላይ እርጋታን አወረደ። ቅርብ የሆነንም መክፈት መነዳቸው። ብዙዎች የተማረኩ ገንዘቦችን የሚወስዷቸው የሆኑን መነዳቸው። አላህም አሸናፊ፤ ጥበበኛ ነው።

وَعَدَكُمُ ٱللَّهُ مَغَانِمَ كَثِيرَةً تَأۡخُذُونَهَا فَعَجَّلَ لَكُمۡ هَٰذِهِۦ وَكَفَّ أَيۡدِيَ ٱلنَّاسِ عَنكُمۡ
وَلِتَكُونَ ءَايَةً لِّلۡمُؤۡمِنِينَ وَيَهۡدِيَكُمۡ صِرَٰطًا مُّسۡتَقِيمًا ﴿٢٠﴾ وَأُخۡرَىٰ لَمۡ تَقۡدِرُواْ عَلَيۡهَا قَدۡ
أَحَاطَ ٱللَّهُ بِهَاۚ وَكَانَ ٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٗا ﴿٢١﴾

**20-21.** (አማኞች ሆይ!) አላህ ብዙዎቹን የምትወስዷቸው የምትወዷቸው የሆኑን ተስፋ አደረገላችሁ። ይህችንም ለእናንተ አስቸኮለላችሁ። ከናንተም የሰዎችን እጆች ከለከለላችሁ ልታመሰግኑና ለምዕመናንም ምልክት እንድትሆን ቀጥተኛውን መንገድ ይመራችሁም ዘንድ (ይህን አደረገላችሁ)። ሌላይቱንም በእርሷ ላይ ገና ያልቻላችኋትን አላህ ያወቃትን (ለእናተ አዘጋጅቷል)። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነውና።

وَلَوۡ قَٰتَلَكُمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَوَلَّوُاْ ٱلۡأَدۡبَٰرَ ثُمَّ لَا يَجِدُونَ وَلِيّٗا وَلَا نَصِيرٗا ﴿٢٢﴾

**22.** እነዚያም በአላህ የካዱት የመካ ሰዎች በተዋጓችሁ ኖሮ ለሽሽት ጀርባዎችን ባዞሩ ነበር። ከዚያ ዘመድም ረዳትም አያገኙም።

سُنَّةَ ٱللَّهِ ٱلَّتِي قَدۡ خَلَتۡ مِن قَبۡلُۖ وَلَن تَجِدَ لِسُنَّةِ ٱللَّهِ تَبۡدِيلٗا ﴿٢٣﴾

**23.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ ያችን ከዚህ በፊት በእርግጥ ያለፈችውን ልማድ ደነገገ። ለአላህ (የማይለወጥን ህግ) መቸም ለውጥን አታገኝም።

وَهُوَ ٱلَّذِي كَفَّ أَيۡدِيَهُمۡ عَنكُمۡ وَأَيۡدِيَكُمۡ عَنۡهُم بِبَطۡنِ مَكَّةَ مِنۢ بَعۡدِ أَنۡ أَظۡفَرَكُمۡ
عَلَيۡهِمۡۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرًا ﴿٢٤﴾

**24.** እርሱ (አላህ) ያ! በመካ ውስጥ በእነርሱ ላይ ካስቻላችሁ በኋላ እጆቻቸውን ከእናንተ ላይ እጃችሁንም ከእነርሱ ላይ የከለከለ ነው። አላህም የምትሰሩትን ነገር ሁሉ ተመልካች ነው።

ከአገር መከፈት (24) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የሁደይቢያ ዕለት ሰማንያ ሰዎች ከነሙሉ መሳሪያዎቻቸው ነብዩ እና ባልደረቦቻቸውን በድንገት ለማጥቃት በማሰብ ከተንኢም ጋር ሲወርዱ በሙስሊሞቹ ተማርከው ወደ ነብዩ (ﷺ) ሲቀርቡና እሳቸውም ነፃ ስለለቀቋቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

هُمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَصَدُّوكُمۡ عَنِ ٱلۡمَسۡجِدِ ٱلۡحَرَامِ وَٱلۡهَدۡيَ مَعۡكُوفًا أَن يَبۡلُغَ مَحِلَّهُۥۚ وَلَوۡلَا
رِجَالٞ مُّؤۡمِنُونَ وَنِسَآءٞ مُّؤۡمِنَٰتٞ لَّمۡ تَعۡلَمُوهُمۡ أَن تَطَـُٔوهُمۡ فَتُصِيبَكُم مِّنۡهُم مَّعَرَّةُۢ بِغَيۡرِ عِلۡمٖۖ
لِّيُدۡخِلَ ٱللَّهُ فِي رَحۡمَتِهِۦ مَن يَشَآءُۚ لَوۡ تَزَيَّلُواْ لَعَذَّبۡنَا ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡهُمۡ عَذَابًا أَلِيمًا ٢٥

**25.** እነሱ ማለት እነዚያ በአላህ የካዱ፣ ከተከበረው መስጊድም የከለከሏችሁ መስዋዕትንም የታሰረ ሲሆን ወደ ስፍራው እንዳይደርስ የከለከሉ ናቸው። የማታውቋቸው ወንድ ምዕመናንና ሴት ምዕመናት ከከሓዲያን ጋር ባልነበሩ ኖሮ ያለ እውቀት እርሱን በረገጣችሁና ከእርሱም በኩል መከፋት የሚነካችሁ ባልሆነ ኖሮ እጆቻችሁን ባላገድን ነበር። አላህ የሚፈልገውን ሰው በእዝነቱም ውስጥ ያስገባ ዘንድ (እጆቻችሁን አገደ)። በተለዩ ኖሮ እነዚያን ከእነርሱ ውስጥ በአላህ የካዱትን አሳማሚን ቅጣት በቀጣናቸው ነበር።

إِذۡ جَعَلَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي قُلُوبِهِمُ ٱلۡحَمِيَّةَ حَمِيَّةَ ٱلۡجَٰهِلِيَّةِ فَأَنزَلَ ٱللَّهُ سَكِينَتَهُۥ عَلَىٰ
رَسُولِهِۦ وَعَلَى ٱلۡمُؤۡمِنِينَ وَأَلۡزَمَهُمۡ كَلِمَةَ ٱلتَّقۡوَىٰ وَكَانُوٓاْ أَحَقَّ بِهَا وَأَهۡلَهَاۚ وَكَانَ ٱللَّهُ بِكُلِّ
شَيۡءٍ عَلِيمٗا ٢٦

**26.** እነዚያን በአላህ የካዱት ደራይቱን የመሀይምነቱትን ደራ በልቦቻቸው ውስጥ ባደረጉ ጊዜ (በቀጣናቸው ነበር)። አላህም በመልዕክተኛው ላይ እና በምዕመናኖቹ ላይ እርጋታውን አወረደ። መጠበቂያይቱንም ቃል አስያዛቸው። በእርሷም ተገቢዎች ባለቤቶቿም ነበሩ። አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነው።

ከአገር መክረፈት (26) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ጁነይድ ቢን ሰቡኡ የተባለ ሶሃባ ጠዋት ከሃዲ ሁኜ ነብዩን ስዋጋ ከስዓት ግን ሙስሊም ሁኜ ከእኔ ጋር ሶስት ወንዶች እና ሰባት ሴቶች ሆነን ከእሳቸው ጋር ተዋጋሁ በእኛ ምክንያት ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው በማለት ዘግቧል። (ሱዩጢ)

لَّقَدۡ صَدَقَ ٱللَّهُ رَسُولَهُ ٱلرُّءۡيَا بِٱلۡحَقِّۖ لَتَدۡخُلُنَّ ٱلۡمَسۡجِدَ ٱلۡحَرَامَ إِن شَآءَ ٱللَّهُ ءَامِنِينَ مُحَلِّقِينَ
رُءُوسَكُمۡ وَمُقَصِّرِينَ لَا تَخَافُونَۖ فَعَلِمَ مَا لَمۡ تَعۡلَمُواْ فَجَعَلَ مِن دُونِ ذَٰلِكَ فَتۡحٗا قَرِيبًا ٢٧

**27.** አላህ ለመልዕክተኛው ህልሙ እውነተኛ ሲሆን አላህ የፈለገ እንደሆነ ፀጥተኞች ሆናችሁ ራሳችሁን ላጭታችሁ አሳጥራችሁ የማትፈሩ ስትሆኑ የተከበረውን መስጊድ በእርግጥ ትገባላችሁ ያለውን በእርግጥ እውነት አደረገለት። (ከእርቁ) ያላወቃችሁትንም ነገር አወቀ። እናም ከዚህም በፊት ቅርብን የመክፈት እርቅ አደረገ።

ከአገር መክፈት (27) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ሁደይቢያ እያሉ ከእሱሀቦቻቸው ጋር ወደ መካ ሲገቡ በሰላም ፀጉራቸው ላጭተው አሳጥረው በመናባቸው አይተው ስለነበር ይህ ሳይሆን (ሁዲይን) ስጦታን በሁደይቢያ ሲያርዱ ያዩ ሙስሊሞች መናቡስ እንዴት ሆነ በማለት ነብዩን ሲጠይቋቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሲዩጢ)።

هُوَ ٱلَّذِىٓ أَرْسَلَ رَسُولَهُۥ بِٱلْهُدَىٰ وَدِينِ ٱلْحَقِّ لِيُظْهِرَهُۥ عَلَى ٱلدِّينِ كُلِّهِۦ ۚ وَكَفَىٰ بِٱللَّهِ شَهِيدًا ﴿٢٨﴾

28. እርሱ (አላህ) ያ፣ መልዕክተኛውን (ነብዩ ሙሐመድን) በመሪ መፅሐፍና በእውነተኛ ሀይማኖት በሃይማኖት ሁሉ ላይ የበላይ ሊያደርገው የላከ ነው። መስካሪነትም በአላህ በቃ።

مُّحَمَّدٌ رَّسُولُ ٱللَّهِ ۚ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ أَشِدَّآءُ عَلَى ٱلْكُفَّارِ رُحَمَآءُ بَيْنَهُمْ ۖ تَرَىٰهُمْ رُكَّعًا سُجَّدًا يَبْتَغُونَ فَضْلًا مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضْوَٰنًا ۖ سِيمَاهُمْ فِى وُجُوهِهِم مِّنْ أَثَرِ ٱلسُّجُودِ ۚ ذَٰلِكَ مَثَلُهُمْ فِى ٱلتَّوْرَىٰةِ ۚ وَمَثَلُهُمْ فِى ٱلْإِنجِيلِ كَزَرْعٍ أَخْرَجَ شَطْـَٔهُۥ فَـَٔازَرَهُۥ فَٱسْتَغْلَظَ فَٱسْتَوَىٰ عَلَىٰ سُوقِهِۦ يُعْجِبُ ٱلزُّرَّاعَ لِيَغِيظَ بِهِمُ ٱلْكُفَّارَ ۗ وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَعَمِلُوا۟ ٱلصَّـٰلِحَـٰتِ مِنْهُم مَّغْفِرَةً وَأَجْرًا عَظِيمًۢا ﴿٢٩﴾

29. የአላህ መልዕክተኛ (ነብዩ) ሙሐመድ እና እነዚያም የእርሱ ጓደኞች በከሐዲያን ላይ ብርቱዎች በመካከላቸው ተዛዛኞች ናቸው። አጎንባሾች፤ ሰጋጆች፤ ሆነው ታያቸዋለህ። ሁልጊዜም ከአላህ ችሮታንና ውዴታን ይፈልጋሉ። ምልክታቸው ከስግደታቸው ፈለግ ስትሆን በፊቶቻቸው ላይ ናት። ይህ በተውራት (የተነገረላቸው) ፀባያቸው ነው። በኢንጅል ውስጥ የተጠቀሰው ምሳሌያቸው ደግሞ ቀንዘሉን እንደ አወጣ አዝመራና (ቀንዘሉን) እንዳበረታታው እንደ ወፈረምና ገበሬዎቹን የሚያስደንቅ ሆኖ በአገዳዎቹ ላይ ተስተካክሎ እንደቆመ (አዝመራ) ነው። ያበረታታቸውና ከሐዲያን በእነርሱ ሊያስቆጭ ነው። አላህ እነዚያን በእሱ ያመኑትንና ከእነርሱ በጎዎችን ተግባራት የሰሩትን ሁሉ ምህረትንና ታላቅ ምንዳን ቃል ገበቶላቸዋል።

### ከአገር መክፈት ከአንቀፅ (1-29) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ለነብዩ (ﷺ) ይቅር የተባለላቸው ጥፋት ታላላቅ ወንጀሎች አለ መሆኑን፤
2. የአላህ ፀጋ መልስ ማመስገን ግዴታ መሆኑን፤
3. አላህ ለነብዩ (ﷺ) እና ለተከታዩቻቸው ያጎናፀፋቸው የትዕግስት ምንዳ፤
4. ከሓዲያን ሙስሊሞች በሚያስገኛት ድልና ደስታ እንደሚለይ።
5. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማዕረግና ክብር፤

6. በአላህና በመልዕክተኛው ነብዩ (ﷺ) ማመንና መልዕክተኛውን መረዳት ግዴታ መሆኑን፤
7. አላህን ማጥራት ግዴታ መሆኑን፤
8. በቃል ኪዳን መገኘት ግዴታ መሆኑን፤
9. ከሁደይቢያ ወደ መዲና ሲጓዙ አላህ መልዕክተኛውንና አማኞችን የኸይበርን ሀብት እንደሚሰጣቸው ቃል መግባቱ፤
10. ከሃዲ አስተሳሰቡ ተግባሩና አንደበቱ የተም መሆኑ ድንቁርናና አለማወቅ አስቀያሚነቱን፤
11. የአንድን ሰው አቅምና ብቃት ለማወቅ መፈተን ተገቢ እንደሆነ፤
12. በኢስላም ዘመቻ የታዘዘባቸው ሕዝቦች የሚፈለግባቸው መስለም ወይም ግብር መክፈል፤
13. በአይነ ስውርነት መሰሎች ችግር ከጂሃድም በመቅረት ችግር እንደሌለው፤
14. አላህ ለታዘዙትና ለአመፅ የገባው የምንዳና የቅጣት ቃል ኪዳን እንማራለን።
15. የበይአተ ሪድዋን ተሳታፊ ሰዎች የተቸራቸው ልቅናና ክብር፤
16. የዑመር ብልሀትና አዋቂነት፤
17. አላህ ለታጋሽ አማኒያን የለገሰው ማካካሻ ትልቅነት፤
18. አላህ ለመልዕክተኛው ነብዩ (ﷺ) የገባው ቀል ኪዳን፤
19. አላህ ለአማኒያን የገባው ቃል ኪዳን፤
20. በየትኛውም አማኝና ከሃዲ የተዋጉበት ጦርነት የኋላ ኋላ እድሉ የአማኒያን እንደሆነ፤
21. ኢህራም አድርጎ ወደ መካ ከመግባት የተከለከለ ሰው ምን ማድረግ እንዳለበት፤
22. ሙስሊሞች ካለማወቅ እንዳይጎዱ ጥንቃቄ ማድረግ እንዳለብን፤
23. በሑደይቢያው ስምምነት በተደረገው ውል ሙስሊሞች የደረሰባቸው ከፍተኛ የሞራል ውድቀት ከባድ እንደነበር፤
24. ኢስላም ትክክለኛ እምነት መሆኑንና ከኢስላም ሌላ ያለ እምነት ውድቅ መሆኑን እንማራለን፤

## በአላህ ፈቃድ የአገር መክፈት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (49)
# የቤት ክፍሎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ሑጁራት)

سُورَةُ الحُجُرَاتِ

### የወረደው በመዲና ነው። የአናቅፅ ብዛት (18) ናቸው።
### የሱረቱ አል ሑጁራት መግቢያ

በመግቢያ ላይ አላህ እና ነብዩ (ﷺ) አንድ ነገር ሳይሉ በአንድ ነገር ላይ ውሳኔ መስጠት እንደሌለብን እኛን ሙስሊሞችን ይከለክላል። በነብዩ ላይ ድምፅን ከፍ ማድረግንም በጥብቅ አውግዞ በአንጻሩም ድምፃቸውን ዝቅ የሚያደርጉትን ሰዎች አሞግሷል። ከነብዩ (ﷺ) ጋር ሊደረግ የሚገባው ዉይይት ስርኣት ሳይጠብቁ እንደጓደኛቸው በስማቸው የሚጠሯቸውንም ይኮረኩማል። ትክክለኛ ሙዕሚኖች የደካማ እምነት ባለቤቶች እና ፋሲቆች የሚያመጡትን ወሬ ማጣትራና ማረጋገጥ እንዳለባቸው መመሪያ ይሰጣል።

የሙስሊሞች መሪዎችም ሁለት የሙዕሚን ቡድን ቢጋጭ ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በግልፅ መክሯል። ሙስሊሞች እርስ በእርሳቸው አንዱ በሌላው እንዳያፌዝ፤ በመጥፎ እንዳይጠረጥረው፤ ነውሩንና ዉስጠ ሚስጥሩን እንዳይከታለው በገሀድ ይከለክላል። ከዚያ እምነት ማለት ዘላኖች በምላሳቸው እንደሚሉት ሳይሆን በልባቸው ላይ ሰርፆ አካልን ለተግባር ያሰገደደ ማለት እንደሆነ በግልፅ ያስተምራል። እያንዳንዳችን በሙስሊሞች ላይ መመፃደቅ እንደማይገባን በግልፅ ይመክራል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تُقَدِّمُواْ بَيۡنَ يَدَيِ ٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعٌ عَلِيمٞ ١

**1.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በአላህና በመልዕክተኛው ፊት ነፍሶቻችሁን አታስቀድሙ። አላህን ፍሩ። አላህ ለሚባለው ሁሉ ሰሚ ለሚፈፅመውን ሁሉ ነገር አዋቂ ነውና።

ከክፍሎች (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከነብዩ (ﷺ) ቀደም ብለው ፆም የሚጀምሩ ሰዎች ስለነበሩ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ያሉ አሉ። (ሱዩጢ)
ወይም የዙልሂጃ አስረኛ ቀን የሚታረደው ከሶላት በፊት ያረደ ሰው ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ተብሏል። (ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَرۡفَعُوٓاْ أَصۡوَٰتَكُمۡ فَوۡقَ صَوۡتِ ٱلنَّبِيِّ وَلَا تَجۡهَرُواْ لَهُۥ بِٱلۡقَوۡلِ كَجَهۡرِ
بَعۡضِكُمۡ لِبَعۡضٍ أَن تَحۡبَطَ أَعۡمَٰلُكُمۡ وَأَنتُمۡ لَا تَشۡعُرُونَ ٢ إِنَّ ٱلَّذِينَ يَغُضُّونَ أَصۡوَٰتَهُمۡ
عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ أُوْلَٰٓئِكَ ٱلَّذِينَ ٱمۡتَحَنَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡ لِلتَّقۡوَىٰۚ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٌ عَظِيمٌ ٣

**2-3.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሆይ!) ድምፆቻችሁን ከነብዩ ድምፅ በላይ ከፍ አታድርጉ። ከፊላችሁ ለከፊሉ እንደሚጮህም ሁሉ በንግግር ለርሱ ስትናገሩ አትጩሁ። እናንተ የማታውቁ ስትሆኑ ስራዎቻችሁ እንዳይበላሹ (ከዚህ ተከልከሉ)። እነዚያ በአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ድምፆቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉ እነዚህ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን አላህን ለመፍራት የመረጣቸው ናቸው። ለእነርሱም ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው።

ከክፍሎች ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሳቢት ቢን ቀይስ የተባለ ሶሃቢ እንዳንዶች እንደሚሉት በጆሮው ላይ የመስማት ችግር ስለነበረበት ድምፁን ከፍ ያደርግ ስለነበር ይህ አንቀፅ ሲወርድ ወይኔ እኔን ነው የሚመለከተው እኔ የእሳት ነኝ በማለቱ ነብዩ ሙሐመደ (ﷺ) የጀነት ነው በማለታቸው ነው።

ከክፍሎች ምዕራፍ (2) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡-
የበኒ ተሚም ቡድን በመጣበት ጊዜ አቡበክር አል. ቃዕቃዕኢብኑ መዕበድን አለቃ አድርጉ ሲሉ ዑመር ደግሞ አቅርዕ ኢብኑ ሀቢስን አለቃ ቢደርጉ ይሻላል ስለ አሉ በዚህ ጊዜ አቡበክር ለዑመር እኔን መንቀፍ ነው እንጂ ሌላ አልፈለክም ሲሏቸው ዑመርም በፍፁም ይህን አላሰብኩም እያሉ ሲከራከሩ ድምፀቸው ከፍ ብሎ ስለነበር ይህ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُنَادُونَكَ مِن وَرَآءِ ٱلْحُجُرَٰتِ أَكْثَرُهُمْ لَا يَعْقِلُونَ ﴿٤﴾ وَلَوْ أَنَّهُمْ صَبَرُوا۟ حَتَّىٰ
تَخْرُجَ إِلَيْهِمْ لَكَانَ خَيْرًا لَّهُمْ ۚ وَٱللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٥﴾

**4-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ ከመኗሪያ ክፍሎቹ ውጭ ሆነው የሚጠሩህ አብዛሀኞቻቸው አያውቁም። ወደ እነርሱም እስክትወጣ ድረስ ዝምብለው በታገሱ ኖሮ ለእነርሱ በላጭ በጎ ተግባር በሆነ ነበር። አላህም እጅግ መሀሪና አዛኝ ነውና።

ከክፍሎች ምዕራፍ (4-5) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ የአረብ ዘላኖች አንድ ላይ ተሰባስበው ስለ ነብዩ (ﷺ) በሰፊው ከተወያዩ በኋላ ይህ ሰውዬ ነብይ ከሆነ እድለኞች ነን ንጉስም ከሆነ በስሩ በለሟል ሆነን እንኖራለን እና እናናግረው ብለው ወደ ነብዩ (ﷺ) ቤት መጥተው ወደ ነብዩ መጥተው ሙሐመድ ሆይ! ወጣ በልልን እያሉ ሲጣሩ ጩኸታቸው ነብዩን አሰለቸ። ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِن جَآءَكُمْ فَاسِقٌۢ بِنَبَإٍ فَتَبَيَّنُوٓا۟ أَن تُصِيبُوا۟ قَوْمًۢا بِجَهَٰلَةٍ
فَتُصْبِحُوا۟ عَلَىٰ مَا فَعَلْتُمْ نَٰدِمِينَ ﴿٦﴾

**6.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ነገረኛ ወሬ ቢያመጣላችሁ በስህተት ላይ ሆናችሁ ህዝባችሁን እንዳትጎዱና ከዚያ በሰራችሁት ነገር ላይ ተፀፃቾች እንዳትሆኑ አረጋግጡ።

*ከክፍሎች ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ወሊድ ኢብኑ ኡቅበህን ዘካ እንዲሰበስብ ወደ በኒ ሙስጠሊቆች ልከውት ቀደም ሲል በጃህሊያ ስለነበረ የእርስ በእርስ ጠብ በመነሳት እነሱ ለአላህና ለመልዕክተኛው አክብረው በድምቀት ሲቀበሉት እሱ ግን ዝግጅቱንን ግርግሩን በመጥፎ ተርጉሞት ሊገድሉት መስሎት ፈርቶ ተመለሰና በኒ ሙስጠሊቆች ዘካ አንሰጥም ከማለታቸው አልፈው ሊገሉኝ ነበር ብሎ ለነብዩ ስሞታ አቀረበ ነብዩም (ﷺ) በነርሱ ተቀይመው ሊዘምቱባቸው አስበው እያሉ ሰዎች ይህን ነገር ሰምተው ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት መልዕክተኛውን መምጣቱን ሰምተን በክብር ለመቀበልና ዛካውን ልንሰጠው በዝግጅት ላይ እያለን ከመንገድ መመለሱን ስንሰማ ምን አልባት የተመለሰው እርስዎ በእኛ ተቆጥተው ተመለስ ብለውት ከሆነ ብለን ነው። የመጣነው ሲሏቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)*

وَٱعۡلَمُوٓاْ أَنَّ فِيكُمۡ رَسُولَ ٱللَّهِۚ لَوۡ يُطِيعُكُمۡ فِي كَثِيرٖ مِّنَ ٱلۡأَمۡرِ لَعَنِتُّمۡ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ
حَبَّبَ إِلَيۡكُمُ ٱلۡإِيمَٰنَ وَزَيَّنَهُۥ فِي قُلُوبِكُمۡ وَكَرَّهَ إِلَيۡكُمُ ٱلۡكُفۡرَ وَٱلۡفُسُوقَ وَٱلۡعِصۡيَانَۚ
أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلرَّٰشِدُونَ ٧ فَضۡلٗا مِّنَ ٱللَّهِ وَنِعۡمَةٗۚ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ٨

**7-8.** በውስጣችሁም የአላህ መልዕክተኛ መኖሩን እወቁ። ከነገሩ በብዙው ነገሮች ቢከተላችሁ ኖሮ በእርግጥ በተቸገራችሁ ነበር። ግን አላህ እምነትን ወደ እናንተ አስወደደ በልቦቻችሁም ውስጥ አጌጠው። ክህደትንና አመጽንም እምቢተኝነትንም ወደናንተ የተጠላ አደረገ። እነዚያ (እምነትን የወደዱ ክሕደትን የጠሉ ሰዎች) እነርሱ ትክክለኛ ቅኖዎቹ ናቸው። ከአላህ በሆነው ችሮታና ፀጋ (ቅኖች ናቸው)። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው።

وَإِن طَآئِفَتَانِ مِنَ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ٱقۡتَتَلُواْ فَأَصۡلِحُواْ بَيۡنَهُمَاۖ فَإِنۢ بَغَتۡ إِحۡدَىٰهُمَا عَلَى ٱلۡأُخۡرَىٰ
فَقَٰتِلُواْ ٱلَّتِي تَبۡغِي حَتَّىٰ تَفِيٓءَ إِلَىٰٓ أَمۡرِ ٱللَّهِۚ فَإِن فَآءَتۡ فَأَصۡلِحُواْ بَيۡنَهُمَا بِٱلۡعَدۡلِ وَأَقۡسِطُوٓاْۖ
إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُقۡسِطِينَ ٩

**9.** ሁለት የምዕምናን ጭፍሮች እርስ በእርስ ቢጋደሉ በመካከላቸው አስታርቁ። ከሁለት አንደኛይቱ በሌላኛይቱ ላይ ወሰን ብታልፍ ያችን ወሰን የምታልፈውን ወደ አላህ ትዕዛዝ እስከምትመጣ ድረስ ተጋደሉ ብትመለስ ግን በመካከላቸው በትክክል አስታርቁ። በነገሩ ሁሉ አስተካክሉ። አላህ አስተካካዩችን ይወዳልና።

*ከክፍሎች ምዕራፍ (9) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ ሶሃቦች ወደ ነብዩ (ﷺ) እየመጡ ዐብደላህ ኢብኑ ኡበይን ቢያናግሩት ጥሩ ነበር እያሉ ሲነግሯቸው ሊያናግሩት እሳቸው በአህያ ላይ ሁነው ሌሎች ሙስሊሞች ደግሞ በግራቸው ሁነው ሄዱ። እዚያ እንደደረሱ ግን ዐብደላህ እባክህን ውጣልኝ የአህያህ ግማት አስቸገረኝ አላቸው በዚህ ጊዜ አንድ ሱሀባ ተነስቶ ወላሂ ከአንተ ሽታ የነብዩ (ﷺ) አህያ ሽታ ይሻላል። አለው። በዚህ ጊዜ አንድ የእሱ ወገን የሆነ ተነስቶ መልስ ሲሰጥ በሁለቱም ወገኖች እልህ ተጋቡና ችግሮች ተፈጠሩ በጫማ በእጅ መመታታት ተጀመረ። ይህን ምክንያት አድርጎ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው።*

إِنَّمَا ٱلۡمُؤۡمِنُونَ إِخۡوَةٞ فَأَصۡلِحُواْ بَيۡنَ أَخَوَيۡكُمۡۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ لَعَلَّكُمۡ تُرۡحَمُونَ ١٠

**10.** ምዕመናኖች ወንድማማቾች ናቸው። በሁለት ወንድሞቻችሁም መካከል አስታርቁ። ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህን ፍሩ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا يَسۡخَرۡ قَوۡمٞ مِّن قَوۡمٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُونُواْ خَيۡرٗا مِّنۡهُمۡ وَلَا نِسَآءٞ مِّن نِّسَآءٍ عَسَىٰٓ أَن يَكُنَّ خَيۡرٗا مِّنۡهُنَّۖ وَلَا تَلۡمِزُوٓاْ أَنفُسَكُمۡ وَلَا تَنَابَزُواْ بِٱلۡأَلۡقَٰبِۖ بِئۡسَ ٱلِٱسۡمُ ٱلۡفُسُوقُ بَعۡدَ ٱلۡإِيمَٰنِۚ وَمَن لَّمۡ يَتُبۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ١١

**11.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ወንዶች በወንዶች አይሳለቁ። ከእነርሱ የበለጡ ሊሆኑ ይከጀላልና። ሴቶችም በሴቶች አይሳለቁ። ከእነርሱ የበለጡ ሊሆኑ ይከጀላልና። ነፍሶቻችሁንም አታነዉሩ በመጥፎ ስሞችም አትጠራሩ። ከእምነት በኋላ መጥፎ ስም ከፋ። ያልተጸጸተም ሰው በእውነት እነርሱ በዳዩቹ ናቸው።

ከክፍሎች ምዕራፍ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሀፍሷና እና አይሻ በዑሙ ሰለማህ አለባበስ አፌዘው ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

በሌላ ሶፍያ ቢንት ሁየይ የነብዩ (ﷺ) ሴቶች አይሁድ እያሉ እያነወሩኝ ነው በማለታቸው ነብዩ ለምን አንቺስ አባቴ ሐሩን፤ አጎቴ ሙሳ ባለቤቴ ሙሐመድ ነው አላልሻቸውም በማለት ሲመልሱላት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

አንድ ሳቢት ቢን ቀይስ የተባለ በእናቱ የሚያነውሩት ሰው ስለነበር አንድ ቀን በሰዎች ፊት ይህን በማንሳት አንገቱን ስላስደፉት ሁለት የነብዩ ሚስቶች ኡሙ ሰለማን ያላግጡባት ስለነበር ሶፍያ ቢንቱ ሁየይ አንዳንድ ሴቶች የሁደየሁዳ ልጅ እያሉ ይሰድቧት ስለነበረና አባቴ ሀሩን አጎቴ ሙሳ ባሌ ሙሐመድ ነው ለምን አትያቸውም ብለዋት ነበር። በእነዚህ ጉዳዮች ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱجۡتَنِبُواْ كَثِيرٗا مِّنَ ٱلظَّنِّ إِنَّ بَعۡضَ ٱلظَّنِّ إِثۡمٞۖ وَلَا تَجَسَّسُواْ وَلَا يَغۡتَب بَّعۡضُكُم بَعۡضًاۚ أَيُحِبُّ أَحَدُكُمۡ أَن يَأۡكُلَ لَحۡمَ أَخِيهِ مَيۡتٗا فَكَرِهۡتُمُوهُۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ تَوَّابٞ رَّحِيمٞ ١٢

**12.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሆይ! ከጥርጣሬን ብዙን ራቁ። ከጥርጣሬ ከፊሉን ኃጢአት ነውና። ነውርንም አትከታተሉ ከፊላችሁም ከፊሉን አይማው አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ሆኖ ሊበላ ይወዳልን? (መብላቱን) ጠላችሁትም*1 (ሀሜቱንም ጥሉት)*2። አላህንም ፍሩ። አላህ ፀፀትን ተቀባይና አዛኝ ነውና።

✶1 (ሀ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ «አጉል ጥርጣሬን ተጠንቀቁ። አጉል ጥርጣሬ ሀሰተኛ ወሬ ነው። የሌሎችን እንከን አትከታተሉ። አንዳችሁ በአንዳችሁ ላይ አትሳለሉ የስለላ ተግባር አትፈፅሙ። በንግድ ላይ ወንድማችሁ ለመግዛት የሚፈልገውን ሸቀጥ እንዳይገዛ ከፍተኛ ዋጋ አትጥሩ። አትመቀኛኙ። አንዳችሁ አንዳችሁን አይጥላ። አንዳች ከአንዳችሁ ጋር ንግግር አታቁሙ። ወንድማማቾች የሆናችሁ የአላህ ባሪያዎች ሁኑ»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሑዘይፋህ እንዲህ ብለዋል፦ ፡ «ሰዎችን እርስ በርሳቸው ለመጋጨት ለማጣላት ወሬ የሚያመላልስ ሰው ጀነት አይገባም።»

(ሐ) ዐብደላህ ኢብኑ አባስ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) በሁለት መቃብሮች አጠገብ አለፉና፦ «እነዚህ ሰዎች በእርግጥ እየተቀጡ ነው። የሚቀጡትም በከባድ ወንጀል አይደለም። አንደኛው ይሸኛው ሲሸና ራሱን ከቆሻሻ አይጠብቅም። ይሸኛው ደግሞ ዘወትር የሚኖረው ሰዎችን በማማት ነው» ከዚያ በኋላ የቴምር እሸት ለምለም ቅርንጫፍ እንዲመጣላቸው ካዘዙ በኋላ ሲመጣላቸው ቅጠሉን ለሁለት ከፍለው አንደኛውን በአንደኛው መቃብር ሌላኛውን በሁለተኛው መቃብር ላይ ከተከሉ በኋላ «ምናልባት እነዚህ ቅርንጫፎች እስኪደርቁ ድረስ የሰዎቹ ቅጣት ይቀንሳል» አሉ።

✶2 ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) «ሐሜት ምን እንደሆነ ታውቃላችሁን?» በማለት ጠየቁት። «አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ» አሏቸው። «ወንድምህን በሌለበት በሚጠላው ነገር ማውሳትህ ነው» አሉ። «የምለው ነገር ከወንድሜ ላይ በተጨባጭ ያለ ከሆነስ?» ተብለው ተጠይቀውም፦ «የምትለው ነገር በተጨባጭ ከርሱ ላይ ካለ አማኸው። ከሌለ ግን በሀሰት ስሙን አጠፋኸው» አሉ።

ቡኻሪና በዘገቡት ሐዲስ አቡበክር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በመሰናበቻ ሐጅ ዕለት በእርድ ቀን ሚና ላይ ባደረጉት ንግግር ውስጥ እንዲህ ብለዋል፦ «ደሞቻችሁ፤ ገንዘቦቻችሁና ክብሮቻችሁ በዚህ ሀገራችሁ ውስጥ በዚህ ወራችሁ ውስጥ ያለው ይህ ቀናችሁ የተከበረ የሆነው ያህል ክብር ናቸው። አዋጅ! መልዕክቱን አደረስኩን?»

አቡ ዳውድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻ እንዲህ ሲሉ አስተላልፈዋል፦ ለነብዩ (ﷺ) እንዲህ «ሶፍያ እንዲህ እንዲህ መሆኗ ይበቃሃል» አልኳቸው አንዳንድ «አጭር ናት» ማለቷ ነበር። ነብዩም (ﷺ)፦ «ከባህር ውሃ ጋር ቢቀላቀል የሚበክለው ቃል ተናገርሽ» አሉኝ። አንድ ሰውም አወሳሁላቸው። «የአንድን ሰው ስም እንደነሳ ይህን ነገር የምሸለም ብሆን እንኳ ማንሳት አልፈልግም።»

አቡዳውድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ወደ ሰማይ እንዳርግ በተደረገኩ ጊዜ የነሀስ ጥፍር ባላቸው ሰዎች አጠገብ አለፍኩ። ፊቶቻቸውንና ደረቶቻቸውን በርሱ ይቧጥጣሉ። እነዚህ እነማን ናቸው? በማለት ጅብሪልን ጠየቅኩት። የሰዎችን ስጋ የሚበሉና ክብራቸውን የሚዳፈሩት ናቸው አለኝ።»

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلنَّاسُ إِنَّا خَلَقْنَـٰكُم مِّن ذَكَرٍ وَأُنثَىٰ وَجَعَلْنَـٰكُمْ شُعُوبًا وَقَبَآئِلَ لِتَعَارَفُوٓا۟ ۚ إِنَّ أَكْرَمَكُمْ عِندَ ٱللَّهِ أَتْقَىٰكُمْ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ عَلِيمٌ خَبِيرٌ ١٣

**13.** እናንተ ሰዎች ሆይ! እኛ ከወንድና ከሴት ፈጠርናችሁ። እንድትተዋወቁም ጎሳዎችና ነገዶች አደረግናችሁ። አላህ ዘንድ በላጫችሁ በጣም አላህን ፈሪያችሁ ብቻ ነው። አላህ ግልፅን አዋቂ ውስጥንም አዋቂ ነው።

ከክፍሎች ምዕራፍ (13) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ሳቢት ኢብኑ ቀይስ ያን ሰውየ በእናቱ ባነወሩ ጊዜ ማን ነው አገሊትን ያነሳ ማን ነው ሲሉ እኔ ነኝ አለ ነብዩ (ﷺ) እስቲ ሰዎችን ተመልከት አሉት ሰዎችን ሲመለከት ምን አየህ አሉት ነጭ ቀይ ጥቁር አላቸው። በተቅዋ እንጂ አንተ ከእነርሱ በምንም አትበልጥም ስለ አሉት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

۞قَالَتِ ٱلْأَعْرَابُ ءَامَنَّا ۖ قُل لَّمْ تُؤْمِنُوا۟ وَلَـٰكِن قُولُوٓا۟ أَسْلَمْنَا
وَلَمَّا يَدْخُلِ ٱلْإِيمَـٰنُ فِى قُلُوبِكُمْ ۖ وَإِن تُطِيعُوا۟ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ
لَا يَلِتْكُم مِّنْ أَعْمَـٰلِكُمْ شَيْـًٔا ۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿١٤﴾

**14.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የአረብ ዘላኖች አምነናል አሉ። አላመናችሁም ግን ሰልመናል በሉ እምነቱም በልቦቻችሁ ውስጥ ገና ጠልቆ አልገባም። አላህንና መልክተኛውንም ብትታዘዙ ከስራዎቻችሁ ምንም አይጎድልባችሁም። አላህ መሀሪ፤ አዛኝ ነውና በላቸው።

إِنَّمَا ٱلْمُؤْمِنُونَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ ثُمَّ لَمْ يَرْتَابُوا۟ وَجَـٰهَدُوا۟ بِأَمْوَٰلِهِمْ
وَأَنفُسِهِمْ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ۚ أُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلصَّـٰدِقُونَ ﴿١٥﴾

**15.** እውነተኛዎቹ ምዕመናን እነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው ያመኑትና ከዚያ ያልተጠራጠሩት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት ሰዎች ብቻ ናቸው። እነዚያ እነርሱ እውነተኞቹ ናቸው።

قُلْ أَتُعَلِّمُونَ ٱللَّهَ بِدِينِكُمْ وَٱللَّهُ يَعْلَمُ مَا فِى ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۚ
وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ ﴿١٦﴾

**16.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማያት ውስጥ ያለውንና በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ ሲሆን አላህን በሃይማኖታችሁ ታስታውቁታላችሁን? በላቸው። አላህ በነገሩ ሁሉ አዋቂ ነው።

يَمُنُّونَ عَلَيْكَ أَنْ أَسْلَمُوا۟ ۖ قُل لَّا تَمُنُّوا۟ عَلَىَّ إِسْلَـٰمَكُم ۖ بَلِ ٱللَّهُ يَمُنُّ عَلَيْكُمْ
أَنْ هَدَىٰكُمْ لِلْإِيمَـٰنِ إِن كُنتُمْ صَـٰدِقِينَ ﴿١٧﴾ إِنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ غَيْبَ ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ
وَٱللَّهُ بَصِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿١٨﴾

**17-18.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በመስለማቸው በአንተ ላይ ይመፃደቃሉ በእስልምናችሁ በእኔ ላይ አትመጻደቁ። ይልቁንም አላህ ወደ ትክክለኛው እምነት ስለመራችሁ ይመፃደቅባችኋል። እውነተኞች ብትሆኑ (መመፃደቅ የሚገባው ለአላህ ብቻ ነው) በላቸው። አላህ የሰማያትንና የምድርን ሩቅ ሚስጢር ያውቃል። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።

**ከክፍሎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-18) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙስሊም የሆነ ሰው የግል ሀሳቡን ከአላህ ቁርኣንና ከነብዩ ሀዲስ ማስቀደም እንደማይችል፤
2. ነብዩ (ﷺ) ቢሞቱም ሀዲሳቸው ሲወሳ ድምፅን ዝቅ ማድረግ እንዳለብን፤
3. በነብዩ መስጊድ ለሚኖር ለተወሰኑ ቀናትም ቢሆን ለትምህርት፤ ለኹጥባ ካልሆነ በስተቀር ድምፅን ከፍ ከማድረግ መታቀብ እንዳለበት፤
4. የነብዩ (ﷺ) ከፍተኛ ማዕረግ፤
5. ሙስሊሞችን ሊጎዳ የሚችል ነገር ሁሉ ተከታትሎ ማጣራት ግዴታ መሆኑን፤
6. አላህ ምእመናን ከቸራቸው ነገሮች ዋናው እምነትን እንዲወዱ አድርጎ ክህደትን እንዲጠሉ ማድረጉ፤
7. ሙስሊሞች በመካከላቸው ያለውን የእርስ በእርስ ችግር ለማስወገድ መጣር የእያንዳንዱ ግዴታ መሆኑ፤
8. አመፀኛ የሆነን ቡድን ስርዓት ለማስገዛት ሙስሊሞች መተባበር እንዳለባቸው፤
9. በየትኛውም ቦታና ጊዜ ፍትሀዊነት አስፈላጊ መሆኑን፤
10. የሙስሊሞች ወንድማማችነት አስፈላጊ መሆኑን፤
11. በሙስሊሞች መካከል አንዱ ሌላውን በተቀጥላ ስም መጥራት አስፀያፊ ተግባር መሆኑን፤
12. እርግጠኛ ማስረጃ የሌለውን ጥርጣሬ መራቅ አስፈላጊ መሆኑን፤
13. በሙስሊሞች ላይ ስለላና ውስጣዊ ነውሮቻቸውን መፈተሽ አስፈላጊ አለመሆኑን፤
14. ሀሜትና አሉባልታ የተከለከለ አደገኛ ወንጀሎች መሆናቸውን፤
15. በዘር በብሄር መፎካከር ክልክል መሆኑንና መተባበርና መደጋገፍ እንደሚገባ፤
16. በአላህ ፍራቻ ካልሆነ በስተቀር አንዱ በሌላው ላይ ክብርና ማዕረግ እንደሌለው፤
17. በኢስላም በእምነት መካከል ያለው ቋንቋዊ ልዩነት ምን እንደሆነ፤
18. ትክክለኛ አማኞች ማለት እዚህ የተወሱትና መሰል መስፈርቶችን ያሟላ መሆኑን፤
19. ማንም ሰው በዋለው ውለታ መመፃደቅ በኢስላም የተጠላና የተወገዘ መሆኑን፤
20. አላህ ሁሉን ነገር እንደሚያውቅና ምንም ነገር እንደማይሰወረው እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የክፍሎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (50)
## የቃፍ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ቃፍ)

سُورَةُ قٓ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (45) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

قٓۚ وَٱلۡقُرۡءَانِ ٱلۡمَجِيدِ ١ بَلۡ عَجِبُوٓاْ أَن جَآءَهُم مُّنذِرٞ مِّنۡهُمۡ فَقَالَ ٱلۡكَٰفِرُونَ هَٰذَا شَيۡءٌ
عَجِيبٌ ٢ أَءِذَا مِتۡنَا وَكُنَّا تُرَابٗاۖ ذَٰلِكَ رَجۡعُۢ بَعِيدٞ ٣

**1-3.** ቃፍ፤* በተከበረው ቁርኣን እምላለሁ (አንተ ትክክል ነህ)። ይልቁንም ከእነርሱ ጎሳ መካከል የሆነ አስፈራሪ ስለመጣላቸው ተደነቁ። ከሓዲያንም ይህ አስደናቂ ነገር ነው አሉ። በሞትንና አፈር በሆን ጊዜ እንመለሳለን? ይህ ሩቅ የሆነ መመለስ ነው አሉ።

* (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

قَدۡ عَلِمۡنَا مَا تَنقُصُ ٱلۡأَرۡضُ مِنۡهُمۡۖ وَعِندَنَا كِتَٰبٌ حَفِيظُۢ ٤ بَلۡ كَذَّبُواْ بِٱلۡحَقِّ لَمَّا
جَآءَهُمۡ فَهُمۡ فِيٓ أَمۡرٖ مَّرِيجٍ ٥

**4-5.** ከእነርሱ አካል ምድር የምታጎድለውን በእርግጥ አውቀናል። እኛም ዘንድ ጠባቂ መጽሐፍ አለ። አልተመለከቱም ይልቁንም ቁርኣን በመጣላቸው ጊዜ አስተባበሉ። እነርሱም በተምታታ ነገር ውስጥ ናቸው።

أَفَلَمۡ يَنظُرُوٓاْ إِلَى ٱلسَّمَآءِ فَوۡقَهُمۡ كَيۡفَ بَنَيۡنَٰهَا وَزَيَّنَّٰهَا وَمَا لَهَا مِن فُرُوجٖ ٦ وَٱلۡأَرۡضَ
مَدَدۡنَٰهَا وَأَلۡقَيۡنَا فِيهَا رَوَٰسِيَ وَأَنۢبَتۡنَا فِيهَا مِن كُلِّ زَوۡجِۭ بَهِيجٖ ٧ تَبۡصِرَةٗ وَذِكۡرَىٰ لِكُلِّ عَبۡدٖ
مُّنِيبٖ ٨ وَنَزَّلۡنَا مِنَ ٱلسَّمَآءِ مَآءٗ مُّبَٰرَكٗا فَأَنۢبَتۡنَا بِهِۦ جَنَّٰتٖ وَحَبَّ ٱلۡحَصِيدِ ٩ وَٱلنَّخۡلَ
بَاسِقَٰتٖ لَّهَا طَلۡعٞ نَّضِيدٞ ١٠ رِّزۡقٗا لِّلۡعِبَادِۖ وَأَحۡيَيۡنَا بِهِۦ بَلۡدَةٗ مَّيۡتٗاۚ كَذَٰلِكَ ٱلۡخُرُوجُ ١١

**6-11.** ወደ ሰማይም ከበላያቸው ስትሆን ለእርሷ ምንም ቀዳዳዎች የሌሏቸው ሆነው እንዴት እንደገነባናትና በከዋክብት እንዳጌጥናት አልተመለከቱምን? ምድርንም ዘረጋናት በእርሷም ውስጥ ጋራዎችን ጣልንባት በውስጧም ከሚያስደስት አይነት ሁሉ አበቀልን። (ይህንን ያደረግነው) ተመላሽ ለሆነ ባሪያ ሁሉ ለማሳየትና ለማስገንዘብ ነው። ከሰማይም ብሩክን ውሃ አወረድን በእርሱም አትክልቶችንና የሚታጨድን አዝመራ ፍሬ አበቀልን። ዘንባባንም ረዛዥም ለእርሷ የተደራረበ እንቡጥ ያላት ስትሆን አበቀልን። ለባሮቹ ሲሳይ ትሆን ዘንድ (አዘጋጀናት)። በእርሱም የሞተችን ሀገር ሕያው አደረግንበት። ከመቃብር መውጣትም፤ ልክ እንደዚሁ ነው።

كَذَّبَتْ قَبْلَهُمْ قَوْمُ نُوحٍ وَأَصْحَٰبُ ٱلرَّسِّ وَثَمُودُ ﴿١٢﴾ وَعَادٌ وَفِرْعَوْنُ وَإِخْوَٰنُ لُوطٍ ﴿١٣﴾
وَأَصْحَٰبُ ٱلْأَيْكَةِ وَقَوْمُ تُبَّعٍ ۚ كُلٌّ كَذَّبَ ٱلرُّسُلَ فَحَقَّ وَعِيدِ ﴿١٤﴾

**12-14.** ከእነርሱ በፊት የኑህ ህዝቦችና የረስስ ሰዎች ሰሙድም አስተባበሉ። ዓድም ፈርዖንም የሉጥ ወንድሞችም። የአይካ* ሰዎችም የቱብበዕ ህዝቦችም ሁሉ መልዕክተኞችን አስተባበሉ። ዛቻየም ተረጋገጠባቸው።

* በአልሒጅር (78) ኛው አንቀፅ ግርጌን ተመልከት።

أَفَعَيِينَا بِٱلْخَلْقِ ٱلْأَوَّلِ ۚ بَلْ هُمْ فِى لَبْسٍ مِّنْ خَلْقٍ جَدِيدٍ ﴿١٥﴾ وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلْإِنسَٰنَ وَنَعْلَمُ
مَا تُوَسْوِسُ بِهِۦ نَفْسُهُۥ ۖ وَنَحْنُ أَقْرَبُ إِلَيْهِ مِنْ حَبْلِ ٱلْوَرِيدِ ﴿١٦﴾

**15-16.** በመጀመሪያው መፍጠር ደከምን? በእውነቱ እነርሱ ከአዲስ መፍጠር በመጠራጠር ውስጥ ናቸው። ሰውንም ነፍሱ በሀሳቡ የምታጫውተውን የምናውቅ ስንሆን በእርግጥ ፈጠርነው። እኛም ከደም ጋኑ ጅማት ይበልጥ ወደ እርሱ ቅርብ ነን።*

* አንነሳኢይ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «የመፃፊያው ብዕር ከሶስት ሰዎች ላይ ላለመመዝገብ ተነስቷል።

1. የተኛ ሰው ከእንቅልፉ እስኪነቃ፤
2. ሕፃን ልጅ ለአቅመ አዳም እስኪደርስ፤
3. የአእምሮ በሽተኛ የሆነ ሰው እስኪድን ድረስ።»

إِذْ يَتَلَقَّى ٱلْمُتَلَقِّيَانِ عَنِ ٱلْيَمِينِ وَعَنِ ٱلشِّمَالِ قَعِيدٌ ﴿١٧﴾ مَّا يَلْفِظُ مِن قَوْلٍ إِلَّا لَدَيْهِ
رَقِيبٌ عَتِيدٌ ﴿١٨﴾ وَجَآءَتْ سَكْرَةُ ٱلْمَوْتِ بِٱلْحَقِّ ۖ ذَٰلِكَ مَا كُنتَ مِنْهُ تَحِيدُ ﴿١٩﴾

**17-19.** ሁለቱ ቃል ተቀባዮች (መላዕክት) ከቀኝና ከግራ ተቀማጮች ሆነው በሚቀበሉ ጊዜ (አስታውስ) ከቃል ምንም አይናገርም፡፡ ከአጠገቡ ተጠባባቂ እና ዝግጁ የሆኑ መላዕክት ያሉበት ቢሆን እንጂ፡፡ የሞትን መከራ እውነቱን ነገር መጣለች (ሰው ሆይ!)፣ ይህ ያ ከእርሱ ትሸሸው የነበርከው ነው ይባላል፡፡

وَنُفِخَ فِي ٱلصُّورِۚ ذَٰلِكَ يَوۡمُ ٱلۡوَعِيدِ ﴿٢٠﴾ وَجَآءَتۡ كُلُّ نَفۡسٖ مَّعَهَا سَآئِقٞ وَشَهِيدٞ ﴿٢١﴾
لَّقَدۡ كُنتَ فِي غَفۡلَةٖ مِّنۡ هَٰذَا فَكَشَفۡنَا عَنكَ غِطَآءَكَ فَبَصَرُكَ ٱلۡيَوۡمَ حَدِيدٞ ﴿٢٢﴾ وَقَالَ
قَرِينُهُۥ هَٰذَا مَا لَدَيَّ عَتِيدٌ ﴿٢٣﴾ أَلۡقِيَا فِي جَهَنَّمَ كُلَّ كَفَّارٍ عَنِيدٖ ﴿٢٤﴾ مَّنَّاعٖ لِّلۡخَيۡرِ مُعۡتَدٖ
مُّرِيبٍ ﴿٢٥﴾ ٱلَّذِي جَعَلَ مَعَ ٱللَّهِ إِلَٰهًا ءَاخَرَ فَأَلۡقِيَاهُ فِي ٱلۡعَذَابِ ٱلشَّدِيدِ ﴿٢٦﴾ ۞ قَالَ
قَرِينُهُۥ رَبَّنَا مَآ أَطۡغَيۡتُهُۥ وَلَٰكِن كَانَ فِي ضَلَٰلِۭ بَعِيدٖ ﴿٢٧﴾ قَالَ لَا تَخۡتَصِمُواْ لَدَيَّ وَقَدۡ
قَدَّمۡتُ إِلَيۡكُم بِٱلۡوَعِيدِ ﴿٢٨﴾ مَا يُبَدَّلُ ٱلۡقَوۡلُ لَدَيَّ وَمَآ أَنَا۠ بِظَلَّٰمٖ لِّلۡعَبِيدِ ﴿٢٩﴾

**20-29.** በቀንዱም ውስጥ ይነፋል ያ ቀን የዛቻው መፈፀሚያ ቀን ነው፡፡ ነፍስም ሁሉ ከእርሷ ጋር ነጅና መስካሪ ያለባት ሆና ትመጣለች፡፡ ከዚህ ነገር በእርግጥ በድንጋጤ ውስጥ ነበርክ ሽፋንህንም ከአንተ ላይ ገለጥንልህ፡፡ ስለዚህ ዛሬ ዓይንህ ስለታም (ያተኮረ) ነው (ይባላል)፡፡ ቁራኛውም (መላዕክ) ይህ ያ እኔ ዘንድ ያለው ቀራቢ ነው ይላል፡፡ ሞገደኛ ከሓዲን ሁሉ በገሀነም ውስጥ ጣሉ፡፡ ለበጎ ስራ ከልካይ በዳይ ተጠራጣሪ የሆነን ሁሉ ጣሉ፡፡ ያንን ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ ያደረገውን በብርቱ ቅጣት ውስጥ ጣሉት (ይባላል)፡፡ ቁራኛው (ሰይጣን) ጌታችን ሆይ፣ እኔ አላሳሳትኩትም ግን ራሱ በሩቅ ስህተት ውስጥ ነበር ይላል፡፡ (አላህ) ወደ እናንተ ዛቻን በእርግጥ ያስቀደምኩ ስሆን እኔ ዘንድ አትጨቃጨቁ ይላቸዋል፡፡ ቃሉ እኔ ዘንድ አይለወጥም እኔም ለባሮቼ ፈፅሞ በዳይ አይደለሁ (ይላቸዋል)፡፡

يَوۡمَ نَقُولُ لِجَهَنَّمَ هَلِ ٱمۡتَلَأۡتِ وَتَقُولُ هَلۡ مِن مَّزِيدٖ ﴿٣٠﴾ وَأُزۡلِفَتِ ٱلۡجَنَّةُ لِلۡمُتَّقِينَ
غَيۡرَ بَعِيدٍ ﴿٣١﴾ هَٰذَا مَا تُوعَدُونَ لِكُلِّ أَوَّابٍ حَفِيظٖ ﴿٣٢﴾ مَّنۡ خَشِيَ ٱلرَّحۡمَٰنَ بِٱلۡغَيۡبِ
وَجَآءَ بِقَلۡبٖ مُّنِيبٍ ﴿٣٣﴾ ٱدۡخُلُوهَا بِسَلَٰمٖۖ ذَٰلِكَ يَوۡمُ ٱلۡخُلُودِ ﴿٣٤﴾ لَهُم مَّا يَشَآءُونَ
فِيهَا وَلَدَيۡنَا مَزِيدٞ ﴿٣٥﴾

30-35. (ሙሐመድ ሆይ!) ለገሀነም ሞላሽን? የምንልበትንና ጭማሪ አለን? የምትልበትን ቀን (አስጠንቅቃቸው)። ገነትም አላህን ለፈሩት ሩቅ ባልሆነ ስፍራ ትቅቀረባላች። ይህ ወደ አላህ ተመላሽና ህግጋቱን ጠባቂ ለሆነ ሁሉ የተቀጠራችሁት ነው (ይባላሉ)። አልረህማንን በሩቅ ሆኖ ለፈራና በንፁህ ልብ ለመጣ ትቅቀረባለች። በሰላም ግቧታ ይህ የመዘውተሪያ ቀን ነው ይባላሉ። ለእነርሱ በውስጧ ሲሆኑ የሚሹት ሁሉ አላቸው እኛም ዘንድ ጭማሪ (አላህን ማየት) አለ።

وَكَمْ أَهْلَكْنَا قَبْلَهُم مِّن قَرْنٍ هُمْ أَشَدُّ مِنْهُم بَطْشًا فَنَقَّبُوا۟ فِى ٱلْبِلَـٰدِ هَلْ مِن مَّحِيصٍ ﴿٣٦﴾
إِنَّ فِى ذَٰلِكَ لَذِكْرَىٰ لِمَن كَانَ لَهُۥ قَلْبٌ أَوْ أَلْقَى ٱلسَّمْعَ وَهُوَ شَهِيدٌ ﴿٣٧﴾

36-37. ከእነርሱም ከቁረይሾች በፊት ከክፍለ ዘመናት ህዝቦች ብዙዎችን እነርሱ በሀያልነት ከእነርሱ ይበልጥ የበረቱ የሆኑትን ማምለጫ ፍለጋ በየሀገሮቹ የመረመሩትን አጥፈተናል ማምለጫ አለን? በዚሁ ውስጥ ለእርሱ ልብ ላለው ወይም እርሱ በህሊናው ጆሮውን የሰጠ ሆኖ ወደ ሚነበብለት ጆሮውን ለጣለ ሰው ግሳጼ አለበት።

وَلَقَدْ خَلَقْنَا ٱلسَّمَـٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ وَمَا بَيْنَهُمَا فِى سِتَّةِ أَيَّامٍ وَمَا مَسَّنَا مِن لُّغُوبٍ ﴿٣٨﴾

38. ሰማያትንና ምድርን በመካከላቸው ያለውንም ሁሉ በስድስት ቀናት ውስጥ በእርግጥ ፈጠርን ድካምም ምንም አልነካንም።

فَٱصْبِرْ عَلَىٰ مَا يَقُولُونَ وَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ قَبْلَ طُلُوعِ ٱلشَّمْسِ وَقَبْلَ ٱلْغُرُوبِ ﴿٣٩﴾
وَمِنَ ٱلَّيْلِ فَسَبِّحْهُ وَأَدْبَـٰرَ ٱلسُّجُودِ ﴿٤٠﴾

39-40. (ነብዩ ሙሐመድ ሆይ) *በሚሉትም ላይ ታገስ ጌታህንም ከማመስገን ጋር ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ከመገብበቷም በፊት አወድሰው። ከሌሊትም አወድሰው ከስገደቶችም በኋላዎች አወድሰው።

* የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፦ ከዕለታት አንድ ቀን ከአላህ መልዕክተኛ ጋር ሳለን ሙሉ የሆነችው የምሽቷ ጨረቃ ተመልክተው፦ «ጌታችሁን ይህችን ጨረቃን እንደምትመለከቷት ሳትቸገሩ ትመለከቱታላችሁ። ስለዚህ ከቻላችሁ ፀሐይ ከመውጣቷና ከመግባቷ በፊት ያሉት ሶላቶች እንዳያመልጧችሁ። ፈፅሟቸውም» ካሉ በኋላ «... ጌታህንም ከማመስገን ጋር ፀሐይ ከመውጣቷ በፊት ከመግባቷም በፊት አወድሰው።» (ቃፍ፡ 9) የሚለውን የቁርኣን አንቀፅ አነበቡ።

وَٱسْتَمِعْ يَوْمَ يُنَادِ ٱلْمُنَادِ مِن مَّكَانٍ قَرِيبٍ ﴿٤١﴾ يَوْمَ يَسْمَعُونَ ٱلصَّيْحَةَ بِٱلْحَقِّ
ذَٰلِكَ يَوْمُ ٱلْخُرُوجِ ﴿٤٢﴾ إِنَّا نَحْنُ نُحْيِۦ وَنُمِيتُ وَإِلَيْنَا ٱلْمَصِيرُ ﴿٤٣﴾ يَوْمَ تَشَقَّقُ ٱلْأَرْضُ
عَنْهُمْ سِرَاعًاۚ ذَٰلِكَ حَشْرٌ عَلَيْنَا يَسِيرٌ ﴿٤٤﴾

**41-44.** (የሚነግርህን) አዳምጥም ጠሪው ከቅርብ ስፍራ በሚጠራበት ቀን ከመቃብራቸው ይወጣሉ። ጩኸቲቱን በእውነቱ የሚሰሙበት ቀን ያ፣ ከመቃብር የመውጫው ቀን ነው። እኛው ሕያው እናደርጋለን። እንገድላለንም። በመጨረሻም ጊዜ መመለሻው ወደ እኛ ብቻ ነው። የሚፈጥኑ ሆነው ምድር ከእነርሱ ላይ የምትሰነጣጠቅበት ቀን የመውጫ ቀን ነው። ይህ በእኛ ላይ ገር የሆነ መሰብሰብ ነው።

نَّحْنُ أَعْلَمُ بِمَا يَقُولُونَۖ وَمَآ أَنتَ عَلَيْهِم بِجَبَّارٍۖ فَذَكِّرْ بِٱلْقُرْءَانِ مَن يَخَافُ وَعِيدِ ﴿٤٥﴾

**45.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ የሚሉትን ሁሉ አዋቂ ነን። አንተም በእነርሱ ላይ አስገዳጅ አይደለህም። ስለዚህ ዛቻየን የሚፈራን ሰው ሁሉ በቁርአን አስታውስ።

**ከቃፍ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-45) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የቁርአንን ትልቅነት በሰፊው፤
2. ሙቶ መነሳትንና የወህይ እርግጠኝነት ማረጋገጥ፤
3. ሙቶ መነሳትና ለምንዳ መከፈል ያለው እርግጠኝነት፤
4. ቀደርን በሰፊው ማስተማር፤
5. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
6. በአካባቢው ያለውን ነገር በትኩረት በማየት መመራመር እንደሚገባና፤
7. ማንም ሰው ወደ ጌታው ንስሀ መግባት አስፈላጊ ነው።
8. ነብዩ (ﷺ) ይደርስባቸው ከነበረው ችግርና ስቃይ ሁሉ ማፅናናት፤
9. ነብዩን (ﷺ) በማስተባበል ላይ የነበሩትን ሰዎች ማውገዝና ማጥላላት
10. የአላህ ሀያልነትና የእውቀት ስፋት፤
11. እያንዳንዱ ሰው በሁለት መልአክ የታጀበ መሆኑ፤
12. ሞት ከፍተኛ ሰከራ (ልፋቶች) እንዳለው፤
13. አማኝ የሆነ ሰው ገና ሳይሞት በአኼራ ያለውን ብሩህ ዕድል እንደሚነገረው፤
14. ሙቶ መነሳትና ለሂሳብ መቅረብ እርግጠኛ መሆኑን ማረጋገጥን
15. ሙቶ መነሳትን በተለያዩ ማስረጃዎች ማረጋገጥ፤
16. በነዚህ አናቅፆች የተጠቀሱትን አስከፊ ባህሪያት መራቅ እንደሚገባ፤
17. የእሳት ሰዎች የነበሩዋቸው ጭቅጭቅ ምን እንደሚመስሉ፤

18. አላህ ማንንም እንደማይበድል፤
19. የአላህ ፍራቻ የሚያጎናፅፈው ክብርና ማዕረግ፤
20. የንስሃ ገቢዎች ትልቅነትና ማዕረጋቸው፤
21. በጀነት ስላሉ ፀጋዎች ሰፊ መረጃ፤
22. አመፀኞችን ማስፈራራትና ማስጠንቀቅ፤
23. በምክር ለመጠቀም ብዙ ቅድም ሁኔታዎች መሟላት እንዳለባቸው።
24. ትዕግስት ለሁሉም ነገር አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
25. ከሶላት በኋላ በየግላችን ዚክርና ዱዓ ማድረግ ተገቢ ስለመሆኑ፤
26. ኢስላማዊ ምክሮችና ግሳፄዎች ህይወት ላላቸው ልቦናዎች ሁሉ ከፍተኛ ጥቅም እንዳላቸው እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የቃፍ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (51)
# የበታኞች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አዝ-ዛሪያት)

سُورَةُ الذَّارِيَاتِ

**በመካ የወረደ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (60) ናቸው።**

**የሱረቱ አዝ-ዛሪያት መግቢያ**

የሙቶ መነሳትን እውነኛነት ለማረጋገጥ በማለት አጠናክሮ ከሓዲያን ስለ ነብዩና ስለቁርኣን የሚሰጡት አንደበት የተጋጨ መሆኑን በድጋሜ በመሀላ ያጠናክራል። በመቀጠል ከሓዲያን በአኼራ ሊደርስባቸው የሚችለውን አደጋ በቅድሚያ ከማስጠንቀቁም በተጨማሪ የትክክለኛ እምነት ተከታዩችን ምንዳም በአጭሩ ዘግቧል። በምድርና ሰማይም ሆነ በየራሳቹ ያለው የአላህ ተአምርና አስገራሚ ነገር ላይ ምርምር ማካሄድ እንዳለብን ያስታውሳል።

ነብዩ ኢብራሂም ከመላኢካ እንግዶቻቸው ጋር ያካሄዱትን ውይይትና ያለፉት ህዝቦች ታሪክ ምን እንደሚመስል ይዘግባል። ከዚያ ወደ ማጠቃለያው ላይ አምልኮ የሰው ልጆችም ሆኑ ጋኔኖች የተፈጠሩለትን ስለመሆኑ በግልፅ አስተምሮ በነብዩ የሚያስተባብል ሁሉ የሚጠብቀው ያው ባለፉት ህዝቦች ላይ የደረሰ መሆኑን በይፋ አውጀ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَٱلذَّٰرِيَٰتِ ذَرۡوٗا ١ فَٱلۡحَٰمِلَٰتِ وِقۡرٗا ٢ فَٱلۡجَٰرِيَٰتِ يُسۡرٗا ٣ فَٱلۡمُقَسِّمَٰتِ أَمۡرًا ٤
إِنَّمَا تُوعَدُونَ لَصَادِقٞ ٥ وَإِنَّ ٱلدِّينَ لَوَٰقِعٞ ٦

**1-6.** መበተንን በታኝ በሆኑት (ነፋሶች) እምላለሁ ከባድ ዝናብን ተሸካሚዎች በሆኑትም (ዳመናዎች)፤ ገር መንሻለልን ተንሻላዩች በሆኑትም (መርከቦች) እምላለሁ። ነገርን ሁሉ አከፋፋዩች በሆኑትም (መላዕክት) እምላለሁ። የምተቀጠሩት ትንሳኤ እውነት ነው። (እንደየስራው ዋጋን ማግኘትም) ኋኝ (የማይቀር ነው)።

وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلۡحُبُكِ ٧ إِنَّكُمۡ لَفِي قَوۡلٖ مُّخۡتَلِفٖ ٨ يُؤۡفَكُ عَنۡهُ مَنۡ أُفِكَ ٩ قُتِلَ
ٱلۡخَرَّٰصُونَ ١٠ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي غَمۡرَةٖ سَاهُونَ ١١ يَسۡـَٔلُونَ أَيَّانَ يَوۡمُ ٱلدِّينِ ١٢ يَوۡمَ هُمۡ عَلَى
ٱلنَّارِ يُفۡتَنُونَ ١٣ ذُوقُواْ فِتۡنَتَكُمۡ هَٰذَا ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تَسۡتَعۡجِلُونَ ١٤

**7-14.** የ (ከዋክብት) መንገዶች ባለቤት በሆነችው ሰማይ እምላለሁ። እናንተ (የመካ ሰዎች) ሆይ! በተለያየ ቃል ውስጥ ናችሁ። ከእርሱ የሚዝዞር ሰው ይዝዞራል። በግምት የሚናገሩ ውሸታሞች ተረገሙ። እነዚያ እነርሱ በሚሸፍን

ስህተት ውስጥ ዘንጊዎች የሆኑት። የዋጋው መስጫው ቀን መቼ እንደሆነ ይጠይቃሉ። (እነርሱ) በእሳት ላይ በሚፈተኑበት ቀን ነው። መከራችሁን ቅመሱ ይህ ያ በእርሱ ትቻኮሉበት የነበራችሁት ነው (ይባላሉ)።

إِنَّ ٱلْمُتَّقِينَ فِى جَنَّـٰتٍ وَعُيُونٍ ﴿١٥﴾ ءَاخِذِينَ مَآ ءَاتَىٰهُمْ رَبُّهُمْ ۚ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ قَبْلَ ذَٰلِكَ
مُحْسِنِينَ ﴿١٦﴾ كَانُوا۟ قَلِيلًا مِّنَ ٱلَّيْلِ مَا يَهْجَعُونَ ﴿١٧﴾ وَبِٱلْأَسْحَارِ هُمْ يَسْتَغْفِرُونَ ﴿١٨﴾
وَفِىٓ أَمْوَٰلِهِمْ حَقٌّ لِّلسَّآئِلِ وَٱلْمَحْرُومِ ﴿١٩﴾

**15-19.** አላህን ፈሪዎቹ በአትክልቶችና በምንጮች ውስጥ ናቸው። ያንን ጌታቸው የሰጣቸውን ተቀባዩች ሆነው በገነት ውስጥ ይሆናሉ። እነርሱ ከዚህ በፊት መልካም ሰሪዎች ነበሩና። ከሌሊቱ ጥቂቱን ብቻ ይተኙ ነበሩ። በሌሊቱ መጨረሻዎችም እነርሱ ምህረትን ይለምናሉ። በገንዘቦቻቸውም ውስጥ ለለማኝና ከልምና ለተከለከለም (በችሮታቸው) መብት አለ።

وَفِى ٱلْأَرْضِ ءَايَـٰتٌ لِّلْمُوقِنِينَ ﴿٢٠﴾ وَفِىٓ أَنفُسِكُمْ ۚ أَفَلَا تُبْصِرُونَ ﴿٢١﴾

**20-21.** በምድርም ውስጥ ለሚያረጋግጡ ሰዎች ምልክቶች አሉ። (ሰዎች ሆይ) በነፍሶቻችሁም ውስጥ ምልክቶች አሉ። ታዲያ አትመለከቱምን?

وَفِى ٱلسَّمَآءِ رِزْقُكُمْ وَمَا تُوعَدُونَ ﴿٢٢﴾ فَوَرَبِّ ٱلسَّمَآءِ وَٱلْأَرْضِ إِنَّهُۥ لَحَقٌّ
مِّثْلَ مَآ أَنَّكُمْ تَنطِقُونَ ﴿٢٣﴾

**22-23.** ሲሳያችሁን የምትቀጠሩትም (ፍዳና ምንዳ) ሰማይ ውስጥ ነው። በሰማይና በምድር ጌታም እምላለሁ። እርሱ እናንተ እንደምትናገሩት ብጤ እርግጠኛ ነው።

هَلْ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ضَيْفِ إِبْرَٰهِيمَ ٱلْمُكْرَمِينَ ﴿٢٤﴾ إِذْ دَخَلُوا۟ عَلَيْهِ فَقَالُوا۟ سَلَـٰمًا ۖ قَالَ
سَلَـٰمٌ قَوْمٌ مُّنكَرُونَ ﴿٢٥﴾ فَرَاغَ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦ فَجَآءَ بِعِجْلٍ سَمِينٍ ﴿٢٦﴾ فَقَرَّبَهُۥٓ إِلَيْهِمْ قَالَ أَلَا
تَأْكُلُونَ ﴿٢٧﴾ فَأَوْجَسَ مِنْهُمْ خِيفَةً ۖ قَالُوا۟ لَا تَخَفْ ۖ وَبَشَّرُوهُ بِغُلَـٰمٍ عَلِيمٍ ﴿٢٨﴾ فَأَقْبَلَتِ
ٱمْرَأَتُهُۥ فِى صَرَّةٍ فَصَكَّتْ وَجْهَهَا وَقَالَتْ عَجُوزٌ عَقِيمٌ ﴿٢٩﴾ قَالُوا۟ كَذَٰلِكِ قَالَ رَبُّكِ ۖ إِنَّهُۥ
هُوَ ٱلْحَكِيمُ ٱلْعَلِيمُ ﴿٣٠﴾

**24-30.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የተከበሩት የኢብራሂም እንግዶች ወሬ መጥቶሃልን? በእርሱም ላይ በገቡና ሰላም ባሉት ጊዜ ምን እንደሆነ (አስታውስ)። ሰላም ግና ያልታወቃችሁ ህዝቦች ናችሁ አላቸው። ወደ ቤተሰቡም ተዘነበለና ወዲያው የሰባ ወይፈን አመጣ። ከዚያ ወደ እነርሱ (አርዶና ጠብሶ) አቀረበው። አትበሉም ወይ? አላቸው። ከእነርሱ መፍራትን በልቡ አሳደረ። አትፍራ አሉት በአዋቂ ወጣት ልጅም አበሰሩት። ሚስቱም እየጮኸች መጣች ፊቷንም መታች መካን አሮጊት ነኝ አለችም። እንደዚህ ጌታሽ ብሏል። እነሆ እርሱ ጥበበኛና አዋቂ ነው አሏት።

*قَالَ فَمَا خَطْبُكُمْ أَيُّهَا ٱلْمُرْسَلُونَ ﴿٣١﴾ قَالُوٓا۟ إِنَّآ أُرْسِلْنَآ إِلَىٰ قَوْمٍ مُّجْرِمِينَ ﴿٣٢﴾ لِنُرْسِلَ
عَلَيْهِمْ حِجَارَةً مِّن طِينٍ ﴿٣٣﴾ مُّسَوَّمَةً عِندَ رَبِّكَ لِلْمُسْرِفِينَ ﴿٣٤﴾ فَأَخْرَجْنَا مَن كَانَ فِيهَا
مِنَ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٣٥﴾ فَمَا وَجَدْنَا فِيهَا غَيْرَ بَيْتٍ مِّنَ ٱلْمُسْلِمِينَ ﴿٣٦﴾ وَتَرَكْنَا فِيهَآ ءَايَةً
لِّلَّذِينَ يَخَافُونَ ٱلْعَذَابَ ٱلْأَلِيمَ ﴿٣٧﴾

**31-37.** *እናንተ መልዕክተኞች ሆይ፣ ታዲያ ነገራችሁ ምንድ ነው? አላቸው። እነርሱም አሉ እኛ ወደ አመፀኞች ህዝቦች ተልከናል። በእነርሱ ላይ ከጭቃ የሆኑን ድናጋዩች ልንለቅባቸው ተላክን። በጌታህ ዘንድ ለድንበር አላፊዎቹ በየስማቸው ምልክት የተደረገባት ስትሆን። ከምዕመናም በእርሷ በከተማቸው ውስጥ የነበሩትን አወጣን። በውስጧም ከሙስሊሞች ከአንድ ቤት ቤተሰቦች በስተቀር አላገኘንም። በውስጧም ለእነዚያ አሳማሚውን ቅጣት ለሚፈሩት ምልክትን አስቀረን።

* ክፍል ሃያ ሰባተኛ

وَفِى مُوسَىٰٓ إِذْ أَرْسَلْنَٰهُ إِلَىٰ فِرْعَوْنَ بِسُلْطَٰنٍ مُّبِينٍ ﴿٣٨﴾ فَتَوَلَّىٰ بِرُكْنِهِۦ وَقَالَ سَٰحِرٌ
أَوْ مَجْنُونٌ ﴿٣٩﴾ فَأَخَذْنَٰهُ وَجُنُودَهُۥ فَنَبَذْنَٰهُمْ فِى ٱلْيَمِّ وَهُوَ مُلِيمٌ ﴿٤٠﴾

**38-40.** በሙሳ ወሬ ውስጥ ወደ ፈርዖን በግልፅ ማስረጃ በላክነው ጊዜ (ምልክትን አደረገ)። ከድጋፍ (ከሰራዊቱ) ጋርም ከእምነት ዞረ። እርሱ ድግምተኛ ወይም እብድ ነው አለ። እርሱንም ሰራዊቱንም ያዝናቸው እርሱ ተወቃሽ ሲሆን በባህር ውስጥ ጣልናቸው።

وَفِى عَادٍ إِذْ أَرْسَلْنَا عَلَيْهِمُ ٱلرِّيحَ ٱلْعَقِيمَ ﴿٤١﴾
مَا تَذَرُ مِن شَىْءٍ أَتَتْ عَلَيْهِ إِلَّا جَعَلَتْهُ كَٱلرَّمِيمِ ﴿٤٢﴾

**41-42.** በዓድም በእነርሱ ላይ መካንን ነፋስ በላክን ጊዜ ምልክት አለ። በላዩ ላይ የመጣችበትን ማኛውም ነገር እንደበሰበሰ አጥንት ያደረገችው ብትሆን እንጂ አትተወውም።

وَفِى ثَمُودَ إِذْ قِيلَ لَهُمْ تَمَتَّعُوا۟ حَتَّىٰ حِينٍ ﴿٤٣﴾ فَعَتَوْا۟ عَنْ أَمْرِ رَبِّهِمْ فَأَخَذَتْهُمُ ٱلصَّـٰعِقَةُ
وَهُمْ يَنظُرُونَ ﴿٤٤﴾ فَمَا ٱسْتَطَـٰعُوا۟ مِن قِيَامٍ وَمَا كَانُوا۟ مُنتَصِرِينَ ﴿٤٥﴾

**43-45.** በሰሙድም ለእነርሱ እስከ ጊዜ (ሞታችሁ) ድረስ ተጣቀሙ። የተባሉ ጊዜ (ምልክት አለ)። ከጌታቸው ትዕዛዝም ኮሩ። እነርሱም እያዩ ጩኸት ያዘቻቸው። መቆምንም ምንም አልቻሉም የሚረዱም አልነበሩም።

وَقَوْمَ نُوحٍ مِّن قَبْلُ ۖ إِنَّهُمْ كَانُوا۟ قَوْمًا فَـٰسِقِينَ ﴿٤٦﴾

**46.** የኑህንም ህዝቦች ከዚህ በፊት አጠፋን እነርሱ አመፀኞች ህዝቦች ነበሩና።

وَٱلسَّمَآءَ بَنَيْنَـٰهَا بِأَيْي۟دٍ وَإِنَّا لَمُوسِعُونَ ﴿٤٧﴾ وَٱلْأَرْضَ فَرَشْنَـٰهَا فَنِعْمَ ٱلْمَـٰهِدُونَ ﴿٤٨﴾
وَمِن كُلِّ شَىْءٍ خَلَقْنَا زَوْجَيْنِ لَعَلَّكُمْ تَذَكَّرُونَ ﴿٤٩﴾

**47-49.** ሰማይንም በሀይል ገነባናት። እኛም በእርግጥ ቻዩች ነን። ምድርንም ዘረጋናት ምን ያማርንም ዘርጊዎች ነን። ትገነዘቡም ዘንድ ከነገሩ ሁሉ ሁለት ተቃራኒ አይነትን ፈጠርን።

فَفِرُّوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ ۖ إِنِّى لَكُم مِّنْهُ نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٥٠﴾ وَلَا تَجْعَلُوا۟ مَعَ ٱللَّهِ إِلَـٰهًا ءَاخَرَ ۖ
إِنِّى لَكُم مِّنْهُ نَذِيرٌ مُّبِينٌ ﴿٥١﴾ كَذَٰلِكَ مَآ أَتَى ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِم مِّن رَّسُولٍ إِلَّا قَالُوا۟
سَاحِرٌ أَوْ مَجْنُونٌ ﴿٥٢﴾ أَتَوَاصَوْا۟ بِهِۦ ۚ بَلْ هُمْ قَوْمٌ طَاغُونَ ﴿٥٣﴾ فَتَوَلَّ عَنْهُمْ فَمَآ أَنتَ
بِمَلُومٍ ﴿٥٤﴾ وَذَكِّرْ فَإِنَّ ٱلذِّكْرَىٰ تَنفَعُ ٱلْمُؤْمِنِينَ ﴿٥٥﴾ وَمَا خَلَقْتُ ٱلْجِنَّ وَٱلْإِنسَ
إِلَّا لِيَعْبُدُونِ ﴿٥٦﴾ مَآ أُرِيدُ مِنْهُم مِّن رِّزْقٍ وَمَآ أُرِيدُ أَن يُطْعِمُونِ ﴿٥٧﴾ إِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلرَّزَّاقُ
ذُو ٱلْقُوَّةِ ٱلْمَتِينُ ﴿٥٨﴾ فَإِنَّ لِلَّذِينَ ظَلَمُوا۟ ذَنُوبًا مِّثْلَ ذَنُوبِ أَصْحَـٰبِهِمْ فَلَا يَسْتَعْجِلُونِ ﴿٥٩﴾
فَوَيْلٌ لِّلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِن يَوْمِهِمُ ٱلَّذِى يُوعَدُونَ ﴿٦٠﴾

**50-60.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ አላህም ሽሹ እኔ ለእናንተ ከእርሱ ግልፅ አስጠንቃቂ ነኝና (በላቸው)። ከአላህም ጋር ሌላን አምላክ አታድርጉ*። እኔ ለእናንተ ከእርሱ የተላኩ። ግልፅ አስፈራሪ ነኝና። (ነገሩ) እንደዚሁ ነው። እነዚያን ከእነርሱ በፊት የነበሩትን ከመልዕክተኛው ማንም አልመጣቸውም። እርሱ ድግምተኛ ወይም እብድ ነው ያሉ ቢሆን እንጂ። በእርሱ (በዚህ ቃል) አደራ ተባብለዋልን? አይደለም እነርሱ ጥጋበኞች ህዝቦች ናቸው። ከእነርሱም ክርክር ዘወር በል ተዋቸው አንተ ምንም ተወቃሽ አይደለህምና። ገስፅም ግሳጼ ምዕመናን ትጠቅማለችና። ጋኔንና ሰውንም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም። ከእነርሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም። እንዲመግቡኝም አልፈልግም። አላህ እርሱ ሰጪና የብርቱ ሀይል ባለቤት ነውና። ለእነዚያም ለበደሉት እንደ ጓደኞቻቸው ፋንታ ብጤ (የቅጣት) ፋንታ አልላቸው። ስለዚህ አያስቸኩሉኝ። ለእነዚያ በአላህ ለካዱት ሰዎች ከዚያ ከሚቀጠሩት ቀናቸው ወዩላቸው።

* የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላፉት እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ጀሀናም ውስጥ ካሉት ሰዎች ትንሽ ቅንጣት ለሚቀጣው ሰው «እውን በምድር ላይ ያለው ነገር ቢኖር መስዋእት ታደርገዋለህ?» ይለዋል። ሰውየውም «አዎን! ይላል። አላህም «በአደም ጀርባ ላይ እያለህ ከዚህ የቀለለ ነገረ ጠይቄህ ነበር። ይኸውም ከኔ ሌላ አምላክን እንዳትይዝ፤ ነገር ግን እምቢኝ ብለህ በአምኮልት ማጋራቱ ላይ ሙጭጭ አልክ» ይለዋል።»

**ከበታኞች ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-60) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሞት በኋላ መነሳት ሐቅ መሆኑን፤
2. ከርሱ የሚዞር ሰው ይዝዞራል በማለት ስለ ቀዷና ቀድር መሳመን፤
3. ድግምተኞችን መርገምና በነሱ ማፌዝ፤
4. ለፈርሃዊያን በጀነት የተዘጋጀላቸውን ፀጋ ማስታወስ፤
5. ከፍርሃዊያን ባህሪያቶች በጥቀቲ ማውሳት፤
6. በነፍሳችን ብቻ ሳይሆን በምንኖርባት መሬትም አያሌ ተአምሮች እንዳሉ፤
7. የሰዎች ሪዝቅ (ሲሳይ) በሰማይ እንደሆነና ከአላህ ብቻ እንጂ ከማንም እንደማይጠየቅ፤
8. የነብዩን ሙሐመድን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤
9. የነብዩ (ﷺ) ከፍተኛ ማዕረግ መግለፅ፤
10. እንግዶችን ማክበር ግዴታ ስለመሆኑ፤
11. የተፈጥሮ ፍርሀት እምነትን እንደማይጎዳ፤
12. መላኢኮች በሰዎች መመሰል እንደሚችሉ፤
13. አመፀኞችን አጥብቆ ማውገዝ፤
14. ትክክለኛ አማኝ ለሆነ ሰው ሙስሊም የሚለውን ቃል መጠቀም የሚቻል ሲሆን ሙስሊም ለተባለው ሁሉ ግን አማኝ የሚለውን ቃል መጠቀም እንደማይገባ፤
15. ስለ ተውሒድ፤ ስለ ነብይነት፤ ስለ ሙቶ መነሳት፤ ሰፊ ማስረጃዎች፤

16. የአላህ ከሃይላት ሁሉ በላይ እንደሆነ፤
17. ሁል ጊዜም የሀሰት አራማጆች እውነተኞችን በሆነ ባልሆነው ስማቸውን ማጥፋት የተለመደ ተግባራቸው መሆኑን፤
18. የሰው ልጆችን ለማጥፋት ከሚያበቋቸው ነገሮች ሁሉ ዋናው የአላህን ትዕዛዝ አለማክበራቸው መሆኑን፤
19. ተውሒድን በልዩ ልዩ ማስረጃዎች በመደገፍ ማስረዳት፤
20. ሁሉም ነገር ወንድና ሴቴ እንዳለው የሚያስተምረው አንቀፅ የቁርኣንን ሳይንሳዊነት ከሚያረጋግጡት አንዱ መሆኑ፤
21. የሽርክን ተግባር አስጠንቀቆ ከመዘዙ ለመውጣት ወደ ፈጣሪው ንስሃ መግባት እንደሚያስፈልገው።
22. በብዙ ሰዎች ዘንድ እውነትን ደብቆ ውሸትን አሽብርቆ በማሳየት የነበሩትን የተሳሳተ መንገድ በመቃወም የሚያስተምርን ሰው ሁሉ ስም ማቆሸሽና ማጉደፍ የተለመደ መሆኑን፤
23. የነፍስያ ኩራትና ትዕቢት የመጥፎ ነገሮችን ሁሉ መንስኤ መሆኑ፤
24. ሰዎችን በጥሩ ነገር ማስታወስ ተገቢ መሆኑን፤
25. ሰዎችንም ሆኑ ጋኔኖችን የተፈጠሩት ለዒባዳ እንደሆነ፤
26. አላህ ከፍጡራን አገልግሎትና ድጋፍ የተብቃቃ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የበታኞች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (52)
## የጡር ጋራ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አጥ-ጡር)

سُورَةُ الطُّورِ

**በመካ የወረደ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (49) ናቸው።**
**የሱረቱ አጥ-ጡር መግቢያ**

በአምስት ታላላቅ ነገሮች ላይ በመማል አስተባባይ ከሓዲያን ላይ ቅጣት እንደማይቀርና የቅጣቱ አይነትን ብዛት ከመግለፅ ቀጥሎ ፈሪሃን አላህ የተዘጋጀላቸውን የጀነት ደስታና መስተንግዶ መሆኑን ይዘግባል። ከራሳቸውም አልፎ የዘመዶቻቸውም ደረጃ ከፍ ያለ እንደሆነ ይገልፃል። ከዚያ በማስከተል ነብዩ (ﷺ) የሁሉ መላክተኛ መሆኑን በግልፅ ያረጋግጣል።

በስተመጨረሻም ነብዩ (ﷺ) ከሓዲያን በሚያስወሩት አሉ ቧልታ መጨነቅ እንደሌለባቸውና በሁሉም መታገስ እንዳለባቸው በማዘዝ መልዕክቱን ይደመድማል። ከሓዲያን ስለ እሳቸውም ሆነ ስለ ቁርኣን ለሚሉት ጆሮ መስጠት እንደሌለባቸው ይመክራል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَٱلطُّورِ ١ وَكِتَٰبٖ مَّسۡطُورٖ ٢ فِي رَقّٖ مَّنشُورٖ ٣ وَٱلۡبَيۡتِ ٱلۡمَعۡمُورِ ٤
وَٱلسَّقۡفِ ٱلۡمَرۡفُوعِ ٥ وَٱلۡبَحۡرِ ٱلۡمَسۡجُورِ ٦

**1-6.** በጡር (ጋራ) እምላለሁ። በተዘረጋው ብራና ላይ በተጻፈው መጽሐፍም በደመቀው ቤትም፤ ከፍ በተረገው ጣራም፤ በሳት በተሞላው ባህርም እምላለሁ።

إِنَّ عَذَابَ رَبِّكَ لَوَٰقِعٞ ٧ مَّا لَهُۥ مِن دَافِعٖ ٨ يَوۡمَ تَمُورُ ٱلسَّمَآءُ مَوۡرٗا ٩
وَتَسِيرُ ٱلۡجِبَالُ سَيۡرٗا ١٠

**7-10.** የጌታህ ቅጣት በእርግጥ ወዳቂ ነው (የማይቀር ነው)*። ለእርሱ ምንም ገፍታሪ የለውም። ሰማይ ብርቱ መዞርን በምትዞርበት ቀን (ይሆናል)። ተራራዎችም መሄድን በሚሄዱበት ቀን።

✴ ጁበይር ኢብኑ ሙጥዒም «ስለ በድር ምርኮኞች ላናግር ወደ መዲና በሄድኩኝ ጊዜ የደረስኩት በመግሪብ ሰዐት ነበርና ከመስጊድ ዉጭ ሁኜ ነቢዩ ሲያነቡት ሰማሁና ልቤ ብጥስ ብሎ የሚሄድ መሰለኝ። ኢስላም ልቤ ላይ ያረፈው በዚያ ቀን ጀምሮነበር የሰለምኩትም ቅጣት እንዳይወርድብኝ ፈርቸ ነው። ከስጋቴ የተነሳ ከተቀመጥኩበት ሳልነሳ ቅጣቱ እንዳይወርድብኝ እየፈራሁኝ ነበር» ብሏል።

ሒሻም ኢብኑ ሐሳን እኔና ማሊክ ኢብኑ ዲናር ወደ ሐሰኑል በስሪ ቤት ሄድንና ስንደርስ የሆነ ሰው ይህን እያነበበ ነበር እዚህ አንቀፅ ላይ ሲደረስ ሐሰንም ሆነ አብረዋቸው የነበሩ ሁሉ አለቀሱ የማሊክ ኢብኑ ዲናርም ፂም ተንቀጠቀጠ ብለዋል።

فَوَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ١١ ٱلَّذِينَ هُمۡ فِي خَوۡضٖ يَلۡعَبُونَ ١٢ يَوۡمَ يُدَعُّونَ إِلَىٰ نَارِ جَهَنَّمَ
دَعًّا ١٣ هَٰذِهِ ٱلنَّارُ ٱلَّتِي كُنتُم بِهَا تُكَذِّبُونَ ١٤ أَفَسِحۡرٌ هَٰذَآ أَمۡ أَنتُمۡ لَا تُبۡصِرُونَ ١٥
ٱصۡلَوۡهَا فَٱصۡبِرُوٓاْ أَوۡ لَا تَصۡبِرُواْ سَوَآءٌ عَلَيۡكُمۡۖ إِنَّمَا تُجۡزَوۡنَ مَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ١٦

**11-16.** ለአስተባባዮችም ሁሉ ያን ጊዜ ወዮላቸው፡፡ ለነዚያ ለእነርሱ በውሸት ውስጥ የሚጫወቱ ለሆኑት ሰዎች፡፡ ወደ ገሀነም እሳት በሀይል መገፍተርን በሚገፈተሩበት ቀን ይህች ያቺ በእርሷ ታስተባብሉባት የነበራችሁት እሳት ናት፡፡ ይህ ፊት ትሉን እንደነበራችሁት ድግምት ነውን? ወይስ እናንተ አታዩምን ግቧት ታገሱም ወይም አትታገሱ በእናንተ ላይ እኩል ነው፡፡ የምትመነዱት ትሰሩት የነበራችሁትን (ፍዳ) ብቻ ነው ይባላሉ፡፡

إِنَّ ٱلۡمُتَّقِينَ فِي جَنَّٰتٖ وَنَعِيمٖ ١٧ فَٰكِهِينَ بِمَآ ءَاتَىٰهُمۡ رَبُّهُمۡ وَوَقَىٰهُمۡ رَبُّهُمۡ عَذَابَ
ٱلۡجَحِيمِ ١٨ كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ هَنِيٓـَٔۢا بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ١٩ مُتَّكِـِٔينَ عَلَىٰ سُرُرٖ مَّصۡفُوفَةٖۖ
وَزَوَّجۡنَٰهُم بِحُورٍ عِينٖ ٢٠ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَٱتَّبَعَتۡهُمۡ ذُرِّيَّتُهُم بِإِيمَٰنٍ أَلۡحَقۡنَا بِهِمۡ ذُرِّيَّتَهُمۡ
وَمَآ أَلَتۡنَٰهُم مِّنۡ عَمَلِهِم مِّن شَيۡءٖۚ كُلُّ ٱمۡرِيِٕۭ بِمَا كَسَبَ رَهِينٞ ٢١

**17-21.** አላህን ፈሪዎቹ በእርግጥ በገነቶችና በፀጋ ውስጥ ናቸው፡፡ ጌታቸው በሰጣቸው ፀጋ ተደሳቾች ሆነው በገነት ውስጥ ናቸው፡፡ የገሀነምንም ስቃይ ጌታቸው ጠበቃቸው፡፡ ትሰሩት በነበራችሁት ምክንያት ተደሳቾች ሆናችሁ ብሉ ጠጡም ይባላሉ፡፡ በተደረደሩ አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች ሆነው በገነት ይኖራሉ፡፡ አይናማዎች በሆኑ ነጫጭ ሴቶችም እናጠናዳቸዋለን፡፡ እነዚያም በአላህ ያመኑና ዝርያቸውም በእውነት የተከተለቻቸው ዝርያቸውን ከእነርሱ ጋር እናስጠጋቸዋለን፡፡ ከስራዎቻቸውም ምንንም አናጎድልባቸውም፡፡ ሰው ሁሉ በሰራው ስራ ተያዢ ነው፡፡

وَأَمۡدَدۡنَٰهُم بِفَٰكِهَةٖ وَلَحۡمٖ مِّمَّا يَشۡتَهُونَ ٢٢ يَتَنَٰزَعُونَ فِيهَا كَأۡسٗا لَّا لَغۡوٞ فِيهَا
وَلَا تَأۡثِيمٞ ٢٣ ۞وَيَطُوفُ عَلَيۡهِمۡ غِلۡمَانٞ لَّهُمۡ كَأَنَّهُمۡ لُؤۡلُؤٞ مَّكۡنُونٞ ٢٤ وَأَقۡبَلَ بَعۡضُهُمۡ
عَلَىٰ بَعۡضٖ يَتَسَآءَلُونَ ٢٥ قَالُوٓاْ إِنَّا كُنَّا قَبۡلُ فِيٓ أَهۡلِنَا مُشۡفِقِينَ ٢٦ فَمَنَّ ٱللَّهُ عَلَيۡنَا
وَوَقَىٰنَا عَذَابَ ٱلسَّمُومِ ٢٧ إِنَّا كُنَّا مِن قَبۡلُ نَدۡعُوهُۖ إِنَّهُۥ هُوَ ٱلۡبَرُّ ٱلرَّحِيمُ ٢٨

**22-28.** ከሚሹትም ሁሉ እሸትንና ስጋን እንጨምርላቸዋለን። በውስጧ መጠጥን ይሰጣጣሉ። በውስጧ ውድቅ ንግግርና መውወንጀልም የለም። ለእነርሱም የሆኑ ወጣቶች ልክ የተሸፈነ ሉል መስለው በእነርሱ ላይ ለማሰላፍ ይዘዋወራሉ የሚጠያየቁ ሆነውም ከፊላቸው በከፊሉ ላይ ይዞራል። እኛ ፊት በቤተሰቦቻችን ውስጥ ከቅጣት ፈሪዎች ነበርን ይላሉ። አላህ በእኛ ላይ ለገሰ። የመርዛም እሳት ቅጣትንም ጠበቀን። እኛ ከዚህ በፊት እንለምነው ነበርን እነሆ እርሱ በጎ ዋይ አዛኝ ነውና ይላሉ።

فَذَكِّرْ فَمَآ أَنتَ بِنِعْمَتِ رَبِّكَ بِكَاهِنٍ وَلَا مَجْنُونٍ ﴿٢٩﴾
أَمْ يَقُولُونَ شَاعِرٌ نَّتَرَبَّصُ بِهِۦ رَيْبَ ٱلْمَنُونِ ﴿٣٠﴾
قُلْ تَرَبَّصُوا۟ فَإِنِّى مَعَكُم مِّنَ ٱلْمُتَرَبِّصِينَ ﴿٣١﴾
أَمْ تَأْمُرُهُمْ أَحْلَٰمُهُم بِهَٰذَآ ۚ أَمْ هُمْ قَوْمٌ طَاغُونَ ﴿٣٢﴾

**29-32.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሰዎችን) አስታውስ አንተም በጌታህ ፀጋ ምክንያት ጠንቋይም እብድም አይደለህም። ይልቁንም የሞትን አደጋ በእርሱ የምንጠባበቅበት የሆነ ባለ ቅኔ ነው ይላሉን? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ተጠባበቁ እኔም ከናንተ ጋር ከሚጠባበቁት ነኝ በላቸው። አእምሮዎቻቸው በዚህ ተግባር ያዟቸዋልን? አይደለም በእውነቱ እነርሱ ወሰን አላፊ ህዝቦች ናቸው።

ከጡር ጋራ ምዕራፉ (31) ኛ አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዳረ አነድዋ ሙሽሪኮች ተሰብስበው ስለ ነብዩ (ﷺ) ሲወያዩ አንዱ ተነስቶ በገመድ እሰሩትና ከእሱ በፊት የነበሩት ዘፋኞች እነ ዙሀይር እና ናቢጋ እንደሞቱ ሁሉ እስከሚሞት ይቆመጥ ስለ አሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

أَمْ يَقُولُونَ تَقَوَّلَهُۥ ۚ بَل لَّا يُؤْمِنُونَ ﴿٣٣﴾ فَلْيَأْتُوا۟ بِحَدِيثٍ مِّثْلِهِۦٓ إِن كَانُوا۟ صَٰدِقِينَ ﴿٣٤﴾
أَمْ خُلِقُوا۟ مِنْ غَيْرِ شَىْءٍ أَمْ هُمُ ٱلْخَٰلِقُونَ ﴿٣٥﴾ أَمْ خَلَقُوا۟ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضَ ۚ
بَل لَّا يُوقِنُونَ ﴿٣٦﴾ أَمْ عِندَهُمْ خَزَآئِنُ رَبِّكَ أَمْ هُمُ ٱلْمُصَيْطِرُونَ ﴿٣٧﴾
أَمْ لَهُمْ سُلَّمٌ يَسْتَمِعُونَ فِيهِ ۖ فَلْيَأْتِ مُسْتَمِعُهُم بِسُلْطَٰنٍ مُّبِينٍ ﴿٣٨﴾

33-38. ወይም (ቁርኣኑን) ቀጠፈው ይላሉን? አይደል በእውነቱ አያምኑም። እውነተኞችም ከሆኑ መሰሉ የሆነን ንግግር ያምጡ። ወይስ ያለ አንዳች ፈጣሪ ተፈጠሩን? ወይስ እነርሱ ፈጣሪዎች ናቸውን? ወይስ ሰማያትንና ምድርን ፈጠሩን? አይደለም! አያረጋግጡም።* ወይስ የጌታ ግምጃ ቤቶች እነርሱ ዘንድ ናቸውን? ወይስ እነርሱ አሸናፊዎች ናቸውን? ወይስ ለእነርሱ በእርሱ ላይ ከሰማይ የሚያዳምጡበት መሰላል አላቸውን? አድማጫቸውም ሰማሁ ቢል ግልፅን አስረጂ ያምጣ።

* ጁበይር ኢብኑ ሙጥዒም የተባሉ ሱሓቢ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) በመግሪብ ይችን ሱራ ሲያነቡ ሰምቼ ከ (35-37) ያሉትን አናቅፅ ሲያነቡ ልቤ ሊበር ቀርቦ ነበር ብለዋል። (ቡኻሪ)
የሃይማኖት አስተማሪዎች ሁሉ ለእለት ህይወታቸው የሚመሩበት በቂ ገንዘብ እስካላቸው ድረስ ሃይማኖትን በማስተማር ደመወዝ ከመብላት መቆጠብ እንዳለባቸው ያስተምራል።

ከጡር ጋራ ምዕራፉ (34) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዑስማን ኢቢኑ አፋን ሰደቃ ሲያበዙ ያያቸው የጡት ወንድማቸው አብደላህ ቢን ሰርህ ምን እየሰራህ ነው ንብረትህን እየጨረስከ ነው ሲላቸው ወንጀሌን ስለፈራሁኝ ነው ይህን የማደርገው አሉት። እሱም ይህችን ግመልህን ከነጭነቷ ስጠኝና እኔ ሀላፊነት ልውሰድልህ ሲላቸው ተስማምተውና ተፃፅፈው ይሰጡት የነበረውን ሰደቃ ሲያቋርጡ ነበር አንቀፁ ከወረደ በኋላ ዑስማን ወደ ትብብራቸው ተመለሱ። (ዋሒዲ)።

أَمْ لَهُ ٱلْبَنَٰتُ وَلَكُمُ ٱلْبَنُونَ ﴿٣٩﴾ أَمْ تَسْـَٔلُهُمْ أَجْرًا فَهُم مِّن مَّغْرَمٍ مُّثْقَلُونَ ﴿٤٠﴾
أَمْ عِندَهُمُ ٱلْغَيْبُ فَهُمْ يَكْتُبُونَ ﴿٤١﴾ أَمْ يُرِيدُونَ كَيْدًا ۖ فَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ هُمُ
ٱلْمَكِيدُونَ ﴿٤٢﴾ أَمْ لَهُمْ إِلَٰهٌ غَيْرُ ٱللَّهِ ۚ سُبْحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يُشْرِكُونَ ﴿٤٣﴾

39-43. ወይስ ለእርሱ ሴቶች ልጆች አሉትን? (የሉትም!) ለእናንተም ወንዶች ልጆች አሏችሁን? ወይስ ዋጋን ትጠይቃቸዋለህን? ስለዚህ እነርሱ በእዳው የተከበዱ ናቸውን? ወይስ ሩቁ ሚስጢር እነርሱ ዘንድ ነውን? ስለዚህ እነርሱ ይፅፋሉን? ወይስ ተንኮልን በአንተ ይሻሉን? እነዚያም የካዱ በተንኮል ተሸናፊዎች ናቸው። ወይስ ለእነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ አላቸውን? አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ ጠራ።

وَإِن يَرَوْا۟ كِسْفًا مِّنَ ٱلسَّمَآءِ سَاقِطًا يَقُولُوا۟ سَحَابٌ مَّرْكُومٌ ﴿٤٤﴾ فَذَرْهُمْ حَتَّىٰ يُلَٰقُوا۟
يَوْمَهُمُ ٱلَّذِى فِيهِ يُصْعَقُونَ ﴿٤٥﴾ يَوْمَ لَا يُغْنِى عَنْهُمْ كَيْدُهُمْ شَيْـًٔا وَلَا هُمْ يُنصَرُونَ ﴿٤٦﴾
وَإِنَّ لِلَّذِينَ ظَلَمُوا۟ عَذَابًا دُونَ ذَٰلِكَ وَلَٰكِنَّ أَكْثَرَهُمْ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٤٧﴾

**44-47.** ከሰማይም ቁራጭን በእነርሱ ላይ ወዳቂ ሆኖ ቢያዩ ኖሮ ይህ የተደራረበ ደመና ነው ይሉ ነበር። ያንንም በእርሱ የሚገደሉበትን ቀናቸውን እስከሚገኙ ድረስ ተዋቸው። ተንኮላቸው ከእነርሱ ምንም የማይጠቅማቸውንና እነርሱም የማይረዱበትን ቀን እስከሚያገኙ ተዋቸው። ለእነዚያም ለበደሉትም ከዚህ ሌላ ቅርብ ቅጣት አለባቸው ግን አብዛሃሀኞቻቸው አያውቁም።

وَٱصۡبِرۡ لِحُكۡمِ رَبِّكَ فَإِنَّكَ بِأَعۡيُنِنَاۖ وَسَبِّحۡ بِحَمۡدِ رَبِّكَ حِينَ تَقُومُ ﴿٤٨﴾
وَمِنَ ٱلَّيۡلِ فَسَبِّحۡهُ وَإِدۡبَٰرَ ٱلنُّجُومِ ﴿٤٩﴾

**48-49.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ለጌታህ ፍረድም ታገስ አንተ በጥበቃችን ውስጥ ነህና ጌታህንም በምታነሳው ጊዜ ማመስገን ጋር አወድስ። ከሌሊቱና በከዋክብት መደበቂያ ጊዜም ንጋት ላይ አወድሰው።

**ከጡር ጋራ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-49) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ሙቶ መነሳት የማይካድ ሀቅ እንደሆነ ማረጋገጥ፤
2. አላህ በፈለገው መማል እንደሚችል፤
3. ስለ ቂያማና ከሓዲያን በቂያማ ቀን ስለሚኖራቸው ባህሪ አጭር መግለጫ ምንዳና ተግባር ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት፤
4. አላህ በፈለገው መማል እንደሚችል፤
5. ከሓዲያን በቂያማ ቀን ስለሚኖራቸው ባህሪ አጭር መግለጫና ምንዳና ተግባር ተመሳሳይ መሆን እንዳለበት፤
6. ስለጀነት ሰዎች ሙሉ መግለጫ፤
7. አላህ ምእመናን የሰጠው ከፍተኛ ማዕረግ ከፍተኛ ተግባር የሌላቸው ዘሮቻቸው እንኳን እንዲከተላቸው ማድረግ፤
8. ማንም ሰው የቂያማ ዕለት በሰራው ተጠያቂ ስለሆነ በዚህች ዱንያ ላይ ሳለ ራሱን ከተጠያቂነት ለማዳን መጣር እንዳለበት፤
9. በዱንያ እያለ ስለ አኼራ ቅጣት ክብደት መስጋትና ንሰሃ መግባት ተገቢ ስለመሆኑ፤
10. ዱዓ በኢስላም የተቸረው ከፍተኛ ማዕረግ፤
11. አዋቂዎች ህዝቡን ማስተማርና ማስታወስ ግዴታ እንዳለባቸው፤
12. የጥንቆላን ተግባር በከፍተኛ ደረጃ ማውገዝ፤
13. ትዕቢትንና ኩራትን የመጥፎ ነገሮች ሁሉ ምንጭ በመሆናቸው ማጥላላትና ማውገዝ፤
14. ውሸት በጠቅላላ የተከለከለ መሆኑንና በተለይም በአላህና በመልዕክተኛው ላይ ይበልጥ መጥፎ መሆኑን፤
15. ተውሒድን በተለያዩ መስረጃዎችን ማረጋገጥ፤
16. የነብዩን ሙሐመድን (ﷺ) ነብይነት በግልፅ ማስረዳት፤

17. የኢጋሪዎችን አዋቂ ተብዬዎች ማጣጣል፤
18. በዳዕዋ ስራ ምክንያት ደመወዝ ወይም ክፍያ መቀበል ተገቢ አለ መሆኑን፤
19. ገይቦችን (ስውር ነገሮችን) ከአላህ ሌላ ምንም እንደማያውቃቸው፤
20. ቁርአን በተናገራቸው ነገሮች ሁሉ ያለው ተአሚነት
21. የቁረይሽ ከሓዲያን የነበራቸውን ትዕቢትና ኩራት መግለፅ፤
22. ነብዩንና (ﷺ) የሳቸውን ፈለግ የተከተሉት ዱአቶች (አስተማሪዎች ሁሉ) መፅናናት፤
23. የግፍ መጨረሻው ከአኼራ በፊት በዱንያ ላይ እንኳን አስቀያሚ እንደሆነ፤
24. አላህ በሚሰጠው ውሳኔ ምንም አይነት ተቃውሞና ቅሬታ ሳያሰሙ መታገስ ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

## የጡር ጋራ ምዕራፍ በአላህ ፈቃድ እዚህ ላይ አበቃ።

ምዕራፍ (53)
# የኮከቡ ምዕራፍ
(ሱረቱ አን-ነጅም)

سُورَةُ النَّجْمِ

## በመካ የወረደ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (62) ናቸው።
## የሱረቱ አን-ነጂም መግቢያ

ምዕራፉ በመጀመሪያ ላይ በመሀላ በማስደገፍ ነብዩን ከሰዎች በሚያስተምሩት ስለሰማ ቤት ነገሩትና በሌላም እውነተኛነት በግልፅ ይጀምራል። ከዚያ የከሓዲያን አመላካከት የዘቀጠና ራሳቸውን በእጃቸው የሰፉትን ጣኦታት ከማመልካቸው በላይ የተለያዩ ስሞች ስጧቸው መላይኮችን የአላህ ሴት ልጆች ናቸው ካለም በኋላ ወንድን ለራሳቸው አድርጉ። ከዚያ ነብዩ የከሓዲያንን ጉዳይ ለአላህ እንደተዋቸው ይመክራል።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَٱلنَّجْمِ إِذَا هَوَىٰ ۝١ مَا ضَلَّ صَاحِبُكُمْ وَمَا غَوَىٰ ۝٢ وَمَا يَنطِقُ عَنِ ٱلْهَوَىٰٓ ۝٣
إِنْ هُوَ إِلَّا وَحْىٌ يُوحَىٰ ۝٤ عَلَّمَهُۥ شَدِيدُ ٱلْقُوَىٰ ۝٥ ذُو مِرَّةٍ فَٱسْتَوَىٰ ۝٦ وَهُوَ بِٱلْأُفُقِ
ٱلْأَعْلَىٰ ۝٧ ثُمَّ دَنَا فَتَدَلَّىٰ ۝٨ فَكَانَ قَابَ قَوْسَيْنِ أَوْ أَدْنَىٰ ۝٩ فَأَوْحَىٰٓ إِلَىٰ عَبْدِهِۦ مَآ
أَوْحَىٰ ۝١٠ مَا كَذَبَ ٱلْفُؤَادُ مَا رَأَىٰٓ ۝١١ أَفَتُمَٰرُونَهُۥ عَلَىٰ مَا يَرَىٰ ۝١٢

**1-12.** በኮከብ በገባ ጊዜ እምላለሁ (እናንተ የመካ ሰዎች ሆይ)፣ ባልደረባችሁ ሙሐመድ ሐቅን አልተሳሳተም ከእውነትም አላፈነገጠም። ከልብ ወለድ ስሜቱም አይናገርም። እርሱ (ቁርኣን) ከአላህ የተወረደ እንጂ ሌላ አይደለም። ሀይለ ብርቱ የሆነው (መልዐኩ ጂብሪል) አስተማረው። የእውቀት ባለቤት የሆነው። ከዚያ በላይኛው አድማስ ላይ ሆኖ ተደላደለ። ከዚያ (መልዐኩ ጂብሪል) ነብዩን ቀረበው። ከዚያም ወረደ። (ከእርሱ) የሁለት ደጋን ጫፎች ያህል ወይም ከዚህ ባነሰ ርቀት ላይ ሆነም። እናም አላህ ለአገልጋዩ (ለሙሐመድ) ማውረድን (መግለፅ የሻውን) አወረደ (ገለፀ)። (ነቢዩም) ያየውን ነገር ሁሉ*1 ልቦናው አላስተባበለውም*2። ታዲያ ባየው ጉዳይ ላይ ትከራከሩታላችሁን?

*1 እዚህ ላይ የተፍሲር ባለሙያዎች እንደሚሉት ነብዩ (ﷺ) አዩት የተባለውን ነገር ምን እንደሆነ ከፍተኛ ክርክር እንዳለ ዘግበዋል። አንዳንዶች እንዳሉት አላህን አዩ ማለት ነው ሲሉ ይህን አባባል በግንባር ቀደምትነት የሚመሩት ታላቁ ሶሀቢ አብደላህ ኢብኑ አባስና ኢክሪመት ናቸው።

ሁለተኛው አባባል ደግሞ የቁርአኑ ዘገባ ያተኮረው ስለመላኩ ጅብሪል በመሆኑ ነብዩ ራሳቸው ጌታዩን አላየሁም በማለት ስላስተማሩ አዩት የተባለው ጅብሪልን ማለት እንጂ አላህን ማለት እንዳልሆነ ይደመድማሉ። በተጨማሪም አላህን አይተዋል የሚለውን አስተምሮት በጥብቅ ይኮንናሉ። የሀዲስ ባለሙያዎችና የተፍሲር ጠበብቶችም የሚደግፉት አባባል ይህንኑ ሁለተኛውን ነው።

✳2 ማሊክ ኢብኑ ሰዐሰዐህ እንዳስተላፉት ነብዩ እንዲህ ብለዋል፦ «እኔ በእንቅልፍና በመንቃት መካከል ቤት ውስጥ ሳለሁ ልክ በሁለት ሰዎች መካከል እንደተኛ ሰው ሆንኩ። በውስጡ ጥበብና እምነት የተሞላበት ከወርቅ የተሰራ ሳህን ወደኔ ቀረበ። ከዚያም ከጉሮሮዬ አንስቶ እስከ ሆዴ ድረስ ያለው ቦታ ተቀደደ። ሆዴም በዘምዘም ውሃ ከተጣበ በኋላ በጥበብና በእምነት ተሞላ። ከዚያም ከበቅሎ ያነሰ ከአህያ ደግሞ ከፍ ያለ ቡራቅ የሚባል እንሰሳ መሰል መጣልኝና ከጅብሪል ጋር ተያይዘን ሄድን። የቅርቢቱ ሰማይ ላይ ስንደርስ ጅብሪል ለሰማያት ዘበኛ «ክፈት» አለው። ዘበኛውም «ማነው?» ሲል ጠየቀ ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» ሲል መለሰ። ዘበኛውም ቀጠለና «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ሲል አሁንም ጥያቄውን ለጅብሪል አቀረበ። ጅብሪልም «ሙሐመድ ነው» ሲል ለጥያቄው መልስ ሰጠ። ዘበኛውም እንደገና «በእርግጥ ተጠርቷልን?» ሲል ጠየቀ። ጅብሪልም «አዎን» ሲል አሁንም መለሰ። ዘበኛውም «እንኳን ደህና መጣ ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው» አለ። እዚያም የሰው ልጆችን አባት አደምን አገኘሁትና ሰላምታ ሰጠሁት። እሱም «ልጄና ነብይ የሆንከው እንኳን ደህና መጣህ!» አለኝ። ጉዟችንን ቀጥለን ሁለተኛው ሰማይ ላይ ስንደርስ «ማነው?» ተባለ። ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» ሲል መለሰ። «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ሲል ዳግመኛ ጠየቀ። ጅብሪል «ሙሐመድ የአላህ ሰላምታና ሰላም በእርሱ ላይ ይሁን» አለ። ለሶስተኛ ጊዜም «እንዲመጣ ተልኮለታልን?» ተብሎ ተጠየቀ። ጅብሪልም «አዎን» ሲል መለሰ። ከዚያም «እንኳን ደህና መጣ! ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው!! ተባለ። እዚያም ዒሳንና ያሕያን አገኘኋቸውና «ወንድምና ነብይ የሆንከው እንኳን ደህና መጣህ!» አሉኝ። ወደ ሶስተኛው ሰማይ ስንደርስ «ማነው?» ተባለ። ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» አለ። «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ተብሎ ሲጠየቀ «ሙሐመድ ነው» ሲል መለሰ። «እንዲመጣ ተልኮለታልን?» ተብሎ ተጠየቀ። «አዎን ሲል መለሰ። ከዚያም «እንኳን ደህና መጣ! ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው!! ተባለ። እዚያም ዩሱፍን አግኝቼ ሰላምታ ሰጠኃቸው። ወደ አራተኛ ሰማይ ስንደርስ «ማነው?» ተባለ። ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» አለ። «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ተብሎ ሲጠየቀ «ሙሐመድ ነው» ሲል መለሰ። «እንዲመጣ ተልኮለታልን?» ተብሎ ተጠየቀ። «አዎን ሲል መለሰ። ከዚያም «እንኳን ደህና መጣ! ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው!! ተባለ። እዚያም ኢድሪስን አግኝቼ ሰላምታ ሰጠኋቸው። እሳቸውም «ወንድምና ነብይ የሆንከው እንኳን ደህና መጣህ!» አሉኝ። ወደ አምስተኛው ሰማይ ሄድን እዚያም ስንደርስ ስንደርስ «ማነው?» ተባለ። ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» አለ። «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ተብሎ ሲጠየቅ «ሙሐመድ ነው» ሲል መለሰ። «እንዲመጣ ተልኮለታልን?» ተብሎ ተጠየቀ። «አዎን ሲል መለሰ። ከዚያም «እንኳን ደህና መጣ! ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው!! ተባለ። እዚያ ሃሩን አግኝች ሰላምታ ሰጠኋቸው እሳቸውም «ወንድምና ነብይ የሆንከው እንኳን ደህና መጣህ!«አሉ ወደ ስድስተኛው ሰማይ ስንደርስም «ማነው?» ተባለ። ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» አለ። «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ተብሎ ሲጠየቀ «ሙሐመድ ነው» ሲል መለሰ። «እንዲመጣ ተልኮለታልን?» ተብሎ ተጠየቀ። «አዎን ሲል መለሰ። ከዚያም «እንኳን ደህና መጣ! ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው!! ተባለ። እዚያ ሙሳን አግኝች ሰላምታ ሰጠኋቸው እሳቸውም «ወንድምና ነብይ የሆንከው እንኳን ደህና መጣህ!«አሉኝ ከዚያም ሳልፋቸው አለቀሱ። «ምን አስለቀሰህ?» ተብለው ሲጠየቁ «ጌታዬ ሆይ! ይህን ወጣት ከኔ በኋላ የተላከ ነብይ ነው።

በተከታዩቹ መካከልም ከኔ ተከታይ በላይ ጀነት ይገባል» አሉ። ወደ ሰባተኛው ሰማይም ስንደርስ «ማነው?» ተባለ። ጅብሪልም «ጅብሪል ነኝ» አለ። «ካንተ ጋር ያለው ማነው?» ተብሎ ሲጠየቀ «ሙሐመድ ነው» ሲል መለሰ። «እንዲመጣ ተልኮለታልን?» ተብሎ ተጠየቀ። «አዎን ሲል መለሰ። ከዚያም «እንኳን ደህና መጣ! ምን የመሰለ ወደር የማይገኝለት አመጣጥ ነው የመጣው! ተባለ። እዚያ ኢብራሂምን አግኝቼ ሰላምታ ሰጠኋቸው እሳቸውም «ልጄና ነብይ የሆንከው እንኳን ደህና መጣህ!» አሉኝ። እዚያም ተገለጠልኝ «በይተል መዕሙርን» ተመለከትኩ። ጅብሪልንም «ይህ ምንድን ነው?» ስል ጠየቅኩት። እሱም «ይህ በይተል መዕሙር ነው በውስጡም በየዕለቱ ሰባ ሺህ መላእክት ይሰግዱበታል። አንድ ጊዜ ከእሱ ከወጡ ተመልሰው አይገቡም» አለኝ። «ሲድረቱል ሙንተሃ» እንድመለከት ተደረግኩኝ። የነበቅ ፍሬዎቿን ተመለከትኩ ቀለሟ የሀጀርን ከተማ አፈር ይመስላሉ። ቅጠሎቹም ልክ የዝሆንን ጆሮዎች ይመስላሉ። ከስሯም አራት ወንዞች ይፈሳሉ። ሁለቱ ድብቅ ሲሆኑ ሁለቱ ደግሞ ግልፆች ናቸው። ጅብሪልን ስለ ወንዞቹ ጠየቅኩት። እሱም «ሁለቱ ድብቅ ወንዞች ጀነት ውስጥ ያሉ ሲሆኑ ሁለቱ ግልፅ ወንዞች ደግሞ የኢፍራጠስና የአባይ ወንዞች ናቸው» አለም። ከዚያም ሃምሳ ሶላቶች ግዴታ ሆኑብኝ። እኔም ተቀበልኩኝና ወደ ሙሳ ተመልሼ ስመጣ «ምን ፈፀምክ?» ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም «ሀምሳ ሶላቶች ግዴታ ሆኑብኝ» አልኳቸው። እሳቸውም «ስለ ሰዎች እኔ ከአንተ በበለጠ አውቃለሁ የኢስራኤል ልጆችን ወደ መታዘዝ ለማምጣት በብርቱ ሞክሬያለሁ። ተከታዩችህ አይችሉትምና ወደ ጌታህ ተመለስና እንዲቀነስልህ ጠይቀው» አሉኝ። እኔም ተመልሼ እንዲቀነስልኝ ጠየቅኩት አርባ አደረጋቸው። አሁንም ጠየቅኩ ሰላሳ አደረጋቸው። አሁንም ጠየቅኩ ሃያ አደረጋቸው። አሁንም ጠየቅኩ አስር አደረጋቸው። አሁንም ሙሳ ጋር ስመጣ መጀመሪያ የነገሩኝን በድጋሚ ነገሩኝ። አሁንም ጠየቅኩ አምስት አደረጋቸው» አልኳቸው። አሁንም እንደበፊቱ ነገሩኝ። እኔም «ለትዕዛዙ አሁን እጅ ሰጥቻለሁ» ስላቸው አላህም እንዲህ ሲል ተጣራ «ግዴታዩን አሳልፌያለሁ ለባሪያዎቼም ቀላል አድርጌያቸዋለሁ። በአንዷ መልካም ስራ አስር ምንዳን እሰጣለሁ።»

وَلَقَدۡ رَءَاهُ نَزۡلَةً أُخۡرَىٰ ﴿١٣﴾ عِندَ سِدۡرَةِ ٱلۡمُنتَهَىٰ ﴿١٤﴾ عِندَهَا جَنَّةُ ٱلۡمَأۡوَىٰٓ ﴿١٥﴾ إِذۡ يَغۡشَى
ٱلسِّدۡرَةَ مَا يَغۡشَىٰ ﴿١٦﴾ مَا زَاغَ ٱلۡبَصَرُ وَمَا طَغَىٰ ﴿١٧﴾ لَقَدۡ رَأَىٰ مِنۡ ءَايَٰتِ رَبِّهِ ٱلۡكُبۡرَىٰٓ ﴿١٨﴾

**13-18.** እርግጥም በሌላም አጋጣሚ ጊዜ አይቶታል። ይኸውም ሲድረተል (በመጨረሻቱ ቁርቁራ አጠገብ) ሙንተሃ በተባለው ዓለም ላይ ነው። እርሷ ዘንድ የመጨረሻ መኗሪያ የሆነችው ጀነት አለች። (ያም ማለት ሲድረይቱን) ሸፋኝ ነገር በሸፈናት ጊዜ ነው። አይኑ አልተዘነበለም። ወሰንም አላለፈም (አልባዘዘም)። ከጌታው ታላላቅ ተዐምሮች ተመልክቷል።

أَفَرَءَيۡتُمُ ٱللَّٰتَ وَٱلۡعُزَّىٰ ﴿١٩﴾ وَمَنَوٰةَ ٱلثَّالِثَةَ ٱلۡأُخۡرَىٰٓ ﴿٢٠﴾ أَلَكُمُ ٱلذَّكَرُ وَلَهُ ٱلۡأُنثَىٰ ﴿٢١﴾
تِلۡكَ إِذٗا قِسۡمَةٞ ضِيزَىٰٓ ﴿٢٢﴾ إِنۡ هِيَ إِلَّآ أَسۡمَآءٞ سَمَّيۡتُمُوهَآ أَنتُمۡ وَءَابَآؤُكُم مَّآ أَنزَلَ ٱللَّهُ بِهَا
مِن سُلۡطَٰنٍۚ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّ وَمَا تَهۡوَى ٱلۡأَنفُسُۖ وَلَقَدۡ جَآءَهُم مِّن رَّبِّهِمُ ٱلۡهُدَىٰٓ ﴿٢٣﴾
أَمۡ لِلۡإِنسَٰنِ مَا تَمَنَّىٰ ﴿٢٤﴾

**19-24.** (መኮች ሆይ!) ስለ ላትና ስለ ዑዛ ስለ ሶስተኛዋ መናትም የምታውቁትን እስቲ ንገሩኝ። ለእናንተ ወንድ ወንድ ለእሱ ግን ሴት ልጅ ታደርጋላችሁን። ይህ ተግባር አድሏዊ ክፍፍል ነው። እነዚህ ጣኦቶች እናንተና አባቶቻችሁ የሰየማችኋቸው ስሞች እንጂ ሌላ አይደሉም። አላህ በአምላክነታቸው ምንም አይነት መረጃ አላወረደም። ጣኦት አምላኪዎች ከጌታቸው የተላከላቸው ቅኑ መመሪያ እያለ የሚከተሉት ግን ጥርጣሬንና ስሜትን ብቻ ነው። የሰው ልጅ የፈለገውን ሁሉ ያገኛልን?

فَلِلَّهِ ٱلۡأٓخِرَةُ وَٱلۡأُولَىٰ ﴿٢٥﴾ ۞ وَكَم مِّن مَّلَكٖ فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ لَا تُغۡنِي شَفَٰعَتُهُمۡ شَيۡـًٔا إِلَّا مِنۢ بَعۡدِ أَن يَأۡذَنَ ٱللَّهُ لِمَن يَشَآءُ وَيَرۡضَىٰٓ ﴿٢٦﴾ إِنَّ ٱلَّذِينَ لَا يُؤۡمِنُونَ بِٱلۡأٓخِرَةِ لَيُسَمُّونَ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةَ تَسۡمِيَةَ ٱلۡأُنثَىٰ ﴿٢٧﴾ وَمَا لَهُم بِهِۦ مِنۡ عِلۡمٍۖ إِن يَتَّبِعُونَ إِلَّا ٱلظَّنَّۖ وَإِنَّ ٱلظَّنَّ لَا يُغۡنِي مِنَ ٱلۡحَقِّ شَيۡـٔٗا ﴿٢٨﴾

**25-28.** መጪውን ዓለምም ሆነ የመጀመሪያው ዓለም የአላህ ብቻ ነው። በሰማያት ውስጥ ካሉ መላዕክት አላህ የሚሻውንና የሚወደውን ለሰው ያማልዱ ዘንድ ከፈቀደላቸው በኋላ እንጂ ምልጃቸው የማይፈይድ አያሌዎች ናቸው። እነዚያ በመጪው ዓለም የማያምኑት መላዕክትን በሴት ስም ይሰይማሉ። ለእነርሱም በእርሱ ጥርጣሬን እንጅ ሌላን አይከተሉም። ጥርጣሬ ደግሞ ሀቅን ምንም አያብቃቃም።

فَأَعۡرِضۡ عَن مَّن تَوَلَّىٰ عَن ذِكۡرِنَا وَلَمۡ يُرِدۡ إِلَّا ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ﴿٢٩﴾ ذَٰلِكَ مَبۡلَغُهُم مِّنَ ٱلۡعِلۡمِۚ إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعۡلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِۦ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِمَنِ ٱهۡتَدَىٰ ﴿٣٠﴾

**29-30.** ከቁርአን አፈንግጦና የዚችን ዓለም ኑሮ እንጂ ሌላ ከማይመኝ ሰው እራስህን አሽሽ። ይህ የእውቀታቸው ጣሪያ (ድካና መጨረሻ) ነው። ጌታህ ግን እርሱ መንገዱን የሳተውን አዋቂ ነው። የተቀናውንም እንዲሁ አዋቂ ነው።

وَلِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ لِيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ أَسَٰٓـُٔواْ بِمَا عَمِلُواْ وَيَجۡزِيَ ٱلَّذِينَ أَحۡسَنُواْ بِٱلۡحُسۡنَى ﴿٣١﴾

**31.** በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የአላህ ነው። እነዚያን ያጠፉትን በተግባራቸው ሊመነዳና እነዚያን መልካም የሰሩት በመልካሚ (በጀነት) ሊመነዳ ነው።

ٱلَّذِينَ يَجۡتَنِبُونَ كَبَٰٓئِرَ ٱلۡإِثۡمِ وَٱلۡفَوَٰحِشَ إِلَّا ٱللَّمَمَۚ إِنَّ رَبَّكَ وَٰسِعُ ٱلۡمَغۡفِرَةِۚ
هُوَ أَعۡلَمُ بِكُمۡ إِذۡ أَنشَأَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ وَإِذۡ أَنتُمۡ أَجِنَّةٞ فِي بُطُونِ أُمَّهَٰتِكُمۡۖ
فَلَا تُزَكُّوٓاْ أَنفُسَكُمۡۖ هُوَ أَعۡلَمُ بِمَنِ ٱتَّقَىٰٓ ٣٢

32. (እነርሱም) እነዚያ ከታላላቅ ወንጀሎችና ከአፀያፊ ተግባሮች ጥቃቅን ጥፋቶች ሲቀሩ የራቁ ሰዎች ናቸው። (ግን ትናንሾቹን የሚማሩ ናቸው)። ጌታህ ምህረተ ሰፊ ነውና። እርሱ ከምድር በፈጠራችሁ ጊዜም ሆነ በእናቶቻችሁ ማሕፀን ውስጥ ሽሎች በሁናችሁበት ጊዜ ያውቃችኋል። ስለዚህ እራሳችሁን አታሞግሱ። እርሱ በትክክል የሚፈራውን ሰው ከሁሉም ይበልጥ አዋቂ ነው።

أَفَرَءَيۡتَ ٱلَّذِي تَوَلَّىٰ ٣٣ وَأَعۡطَىٰ قَلِيلٗا وَأَكۡدَىٰٓ ٣٤
أَعِندَهُۥ عِلۡمُ ٱلۡغَيۡبِ فَهُوَ يَرَىٰٓ ٣٥

33-35. ያን ከእምነት የሸሸውን እስቲ ንገረኝ። ጥቂትን ብቻ ሰጥቶ ያቋረጠ (አየህን?)። ለመሆኑ የሚያውቀው የሩቅ ሚስጢር አለውን? እናም እርሱ ያያልን?።

أَمۡ لَمۡ يُنَبَّأۡ بِمَا فِي صُحُفِ مُوسَىٰ ٣٦ وَإِبۡرَٰهِيمَ ٱلَّذِي وَفَّىٰٓ ٣٧ أَلَّا تَزِرُ وَازِرَةٞ وِزۡرَ
أُخۡرَىٰ ٣٨ وَأَن لَّيۡسَ لِلۡإِنسَٰنِ إِلَّا مَا سَعَىٰ ٣٩ وَأَنَّ سَعۡيَهُۥ سَوۡفَ يُرَىٰ ٤٠ ثُمَّ يُجۡزَىٰهُ
ٱلۡجَزَآءَ ٱلۡأَوۡفَىٰ ٤١ وَأَنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلۡمُنتَهَىٰ ٤٢

36-42. ወይስ ለሙሳና በዚያ የታዘዘውን በተሟላ መልኩ በፈፀመው በኢብራሂም መፅሐፍ ውስጥ ያለው አልተነገረውምን?። ይኸውም ወንጀለኛ ነፍስ የሌላውን ነፍስ ወንጀል አትሸከምም። የሰው ልጅ የለፋበትን ብቻ እንጂ ሌላ የለውም።* የሰራው ሁሉ ወደ ፊት ይታያል። ከዚያ ጌታውን ሙሉ ምንዳውን ይመነዳዋል። የሁሉም መጨረሻው ወደ ጌታህ ብቻ ነው።

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል:- «አንድ ሰው ሲሞት ከሶስት ስራዎቹ በስተቀር ሌሎች ስራዎቹ ያቆማሉ። እነርሱም:-

1. ቀጣይነት ያለው ምፅዋት፤
2. ጠቃሚነት ያለው እውቀት፤
3. ዱዓዕ የሚያደርግለት መልካም ልጅ»

وَأَنَّهُۥ هُوَ أَضۡحَكَ وَأَبۡكَىٰ ﴿٤٣﴾ وَأَنَّهُۥ هُوَ أَمَاتَ وَأَحۡيَا ﴿٤٤﴾ وَأَنَّهُۥ خَلَقَ ٱلزَّوۡجَيۡنِ ٱلذَّكَرَ
وَٱلۡأُنثَىٰ ﴿٤٥﴾ مِن نُّطۡفَةٍ إِذَا تُمۡنَىٰ ﴿٤٦﴾ وَأَنَّ عَلَيۡهِ ٱلنَّشۡأَةَ ٱلۡأُخۡرَىٰ ﴿٤٧﴾ وَأَنَّهُۥ هُوَ أَغۡنَىٰ
وَأَقۡنَىٰ ﴿٤٨﴾ وَأَنَّهُۥ هُوَ رَبُّ ٱلشِّعۡرَىٰ ﴿٤٩﴾

43-49. እርሱ ያ ያሳቀና ያስለቀሰ ነው። እርሱ ያ የገደለና ሕያው ያደረገ ነው። እርሱ ያ ሁለትን አይነቶች ጥንድን ወንድና ሴትን የፈጠረ ነው። ይኸውም ከፍቶት ጠብታ በማሕፀን ውስጥ በምትፈሰስ ጊዜ ነው። ሌላውን ማስገኘት በእርሱ ላይ ነው። እነሆ እርሱ ያ ሀብትን የሰጠና ያብቃቃ ነው። እነሆ እርሱ የሺዕራ ጌታ ነው።

وَأَنَّهُۥٓ أَهۡلَكَ عَادًا ٱلۡأُولَىٰ ﴿٥٠﴾ وَثَمُودَاْ فَمَآ أَبۡقَىٰ ﴿٥١﴾ وَقَوۡمَ نُوحٖ مِّن قَبۡلُۖ
إِنَّهُمۡ كَانُواْ هُمۡ أَظۡلَمَ وَأَطۡغَىٰ ﴿٥٢﴾ وَٱلۡمُؤۡتَفِكَةَ أَهۡوَىٰ ﴿٥٣﴾ فَغَشَّىٰهَا مَا غَشَّىٰ ﴿٥٤﴾

50-54. እነሆ እርሱ የቀድሞ ሰዎችን የአድ ሕዝቦችን አጠፋ። ሰሙድንም አጠፋ። አንድንም አላስቀረም። በፊትም የኑህን ህዝቦች አጥፍቷል። እነርሱ እጅግ በዳዮችና በጣም አመፀኞች ነበሩና ነው። የተገለበጠችውን ከተማ (የሉጥን ህዝቦች) አጠፋን። ያሸፈናትንም አሸፈናት። (በደንጋይ ዝናብ አለበሳት)።

فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكَ تَتَمَارَىٰ ﴿٥٥﴾

55. (የሰው ልጅ ሆይ)፣ ከጌታህ ፀጋዎች በየትኛው ነው የምትጠራጠረው።

هَٰذَا نَذِيرٞ مِّنَ ٱلنُّذُرِ ٱلۡأُولَىٰٓ ﴿٥٦﴾ أَزِفَتِ ٱلۡأٓزِفَةُ ﴿٥٧﴾ لَيۡسَ لَهَا مِن دُونِ ٱللَّهِ كَاشِفَةٌ ﴿٥٨﴾
أَفَمِنۡ هَٰذَا ٱلۡحَدِيثِ تَعۡجَبُونَ ﴿٥٩﴾ وَتَضۡحَكُونَ وَلَا تَبۡكُونَ ﴿٦٠﴾ وَأَنتُمۡ سَٰمِدُونَ ﴿٦١﴾

56-61. ይህ ከቀድሞዎቹ አስጠንቃቂዎች አንዱ ነው። ቀራቢቱ (ትንሳኤ) ቀረበች። ለእርሷ ከአላህ በስተቀር ገላጭ የላትም። በዚህ ዘገባ ትደነቃላችሁን?። ትስቃላችሁን? አታለቅሱምን?። እናንተ ዘወትር ዘንጊዎች ናችሁን?።

فَٱسۡجُدُواْۤ لِلَّهِۤ وَٱعۡبُدُواْ۩ ﴿٦٢﴾

62. ለአላህ ስገዱ በብቸኝነትም አምልኩትም።

**ከኮከብ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-62) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት በግልፅ ማስረጃ ማረጋገጥ፤
2. ነብዩን (ﷺ) ከስሜታዊ ተግባር ማፅዳት፤
3. ልዩ ልዩ የመላኩ ጅብሪል ባህሪያት መግለፅ፤
4. ነብዩ (ﷺ) መላኩ ጅብሪልን በተፈጠረው ባህሪው ሁለት ጊዜ ማየታቸውን፤
5. የበይተል መቅዲስ ጉዞዋቸውንና ወደ ሰማይ የማረጋቸውን ታሪክ በይፋ ማፅደቅ፤
6. የሽርክ ተግባሪዎችን በምሳሌ ማውገዝ፤
7. በየትኛውም ዘመንና ቦታ ያሉ ሙሽሪኮች ስሜታቸውን እንጂ ሌላ ነገርን እንደማይከተሉ፤
8. ሰዎች በምኞታቸው ብቻ ምንም ነገር እንደማይሰጡ፤
9. ዱንያም እንደ አኼራ ሁሉ የአላህ በመሆኑ ዱንያም ቢሆን በአላህ እንጂ በሌላ ከማንም እንደማይጠየቅ፤
10. የትኛውም የሽምግልና ተግባር ሁለት ነገሮችን ከላሟላ በስተቀር ፋይዳ እንደሌለው እነሱም፡-
    1ኛ ለሽምጋዩ የአላህ ሙሉ ፈቃድ መኖሩ ሲሆን፤
    2ኛ ለተሽምጋዩ የአላህ ውዴታን ማግኘት የሚሉት ናቸው።
11. አብዛሀኛው በሽታ በአኼራ ከሚያገኙ ልቦች የሚመነጭ መሆኑን፤
12. በምድር ላይ ያለ ብዙ ጥፋቶችን ካለ ማወቅ የተነሱ መሆናቸውን፤
13. ማቴሪያሊስቶች በኢስላም ላይ ከፍተኛ አደጋ ፈጣሪዎች መሆናቸውን ነው።
14. የአላህን ብቸኛ ጌትነት በማስረጃዎች ማረጋገጥ፤
15. የአላህን ፍትህዊነት በገሀድ ማረጋገጥ፤
16. የአላህን ችሎታና እውቀት ጥበብም ስፋት ማሳየት፤
17. የሰው ልጅ ሊጎዳውም ሆነ ሊጠቅመው የሚችለው ራሱ አስቦና አውቆት የሚፈፅመው ተግባር መሆኑ፤
18. በየትኛውም ቦታና ዘመን የሚፈጠሩ ሙሽሪክ ግፈኞች መሰሎቻቸው ያጋጠማቸው አይነት አደጋ እንዳያጋጥማቸው አስቀድሞ ማስጠንቀቅ፤
19. የአላህን ብቸኛ ጌትነትና አሀዳዊ ስልጣን ማረጋገጥ፤
20. የአላህ ፍላጎት ሀያልን ብቸኝነት፤
21. ምንዳ ከተግባር ጋር ተመጣጣኝ ወይም ተመሳሳይ መሆን፤
22. ጥቃቅን ወንጀሎች ከፍተኛ ወንጀሎችን በመከልከል ብቻ እንደሚሰረዙልን፤
23. ራስን ማሞገስና ራስን መካብ ተገቢ አለመሆኑን፤
24. የቂያማ ቀን መቅረብ ማብሰር፤
25. በስሜት ተውጦ መሳቅና መንከትከት መጥፎ ምግባር ስለመሆኑ፤
26. በአላህ ፍራቻ ማልቀስ ተገቢ መሆኑን፤
27. ዘፈንና አሉቧልታ ጨዋታዎች ተገቢ አለመሆናቸውን፤
28. ማጥራት ተገቢ ስለመሆኑ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የኮከብ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (54)
# የጨረቃው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ቀመር)

سُورَةُ القَمَرِ

### በመካ ነው የወረደ። የምእራፉ አናቅፅ (55) ናቸው።
### የሱረቱ አል ቀመር መግቢያ

ምዕራፉ በመግቢያ ላይ ስለቂያማ ቀን በመቅረብ አስታውሶ አስጠንቅቆ ከሀዲዎችም አይነት ታዐምር ቢመለከቱ የማያምኑ ፍጡሮች መሆናቸውን ገልፆ ነብዩ (ﷺ) ለእነሱ ምንም አይነት ጭንቀት እንዳይዛቸውና እነሱ ተገቢውን ምንዳ ሊያገኙ የሚችሉ ከቀብር የሚወጡበት ቀን መሆኑን በማስረዳት ያፅናናል። በመቀጠልም ያለፉት ህዝቦች ነብያትን እንዴት እንዳስተባበሉና ቅጣት እንዴት እንደመጣባቸው በማከታተል ዘግቦ የመካ ከሓዲያን ካለፉት ህዝቦች በበለጠ ብርቱ እንዳልሆነ ደምድሞ በግንባራቸው የሚጎተቱበትን አስታውሶ በማስፈራራት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱقۡتَرَبَتِ ٱلسَّاعَةُ وَٱنشَقَّ ٱلۡقَمَرُ ١ وَإِن يَرَوۡاْ ءَايَةٗ يُعۡرِضُواْ وَيَقُولُواْ سِحۡرٞ مُّسۡتَمِرّٞ ٢
وَكَذَّبُواْ وَٱتَّبَعُوٓاْ أَهۡوَآءَهُمۡۚ وَكُلُّ أَمۡرٖ مُّسۡتَقِرّٞ ٣ وَلَقَدۡ جَآءَهُم مِّنَ ٱلۡأَنۢبَآءِ مَا فِيهِ
مُزۡدَجَرٌ ٤ حِكۡمَةُۢ بَٰلِغَةٞۖ فَمَا تُغۡنِ ٱلنُّذُرُ ٥

**1-5.** ሰዓቲቱ (የትንሳኤ ቀን) ተቃረበች።* ጨረቃም ተገመሰ። ከሓዲያን ተዐምርንም ባዩ ኑሮ እንቢ ብለው በዞሩ ነበር። ይህ ዘውታሪ ድግምት ነው ይላሉ። አስተባበሉም ዝንባሌዎቻቸውንም ተከተሉ። ነገርም ሁሉ ወሰን አለው ረጊ ነው። ከዜናዎቹ በእርሱ ውስጥ መገሰጫ የሚሆን ነገር ያለበት በእርግጥ መጣላቸው። ሙሉ ከሆነ ጥበብ (መጣላቸው)። ግን አስፈራሪዎች (አያብቃቁም) አያድኑም።

فَتَوَلَّ عَنۡهُمۡۘ يَوۡمَ يَدۡعُ ٱلدَّاعِ إِلَىٰ شَيۡءٖ نُّكُرٍ ٦ خُشَّعًا أَبۡصَٰرُهُمۡ يَخۡرُجُونَ مِنَ ٱلۡأَجۡدَاثِ
كَأَنَّهُمۡ جَرَادٞ مُّنتَشِرٞ ٧ مُّهۡطِعِينَ إِلَى ٱلدَّاعِۖ يَقُولُ ٱلۡكَٰفِرُونَ هَٰذَا يَوۡمٌ عَسِرٞ ٨

**6-8.** ከእነርሱም ተውና ዞር። ይልቁንስ ጠሪው መላዕክ ወደ አስደንጋጭ ነገር የሚጠራበትን ቀን (አስታውስ)። ዓይኖቻቸው ያቀረቀሩ ሆነውና ፍፁም የተበተኑ አንበጣ መስለው ከመቃብሮቻቸው ይወጣሉ። ወደ ጠሪው አንገቶቻቸውን ሳቢዎችና ቸኳዩች ሆነው (ይወጣሉ)። ከሓዲያን (ያን ጊዜ ምን ይላሉ?)። ይህ ብርቱ ቀን ነው ይላሉ።

✷ ከጨረቃ ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩ (ﷺ) ጊዜ አንድ ቀን ጨረቃ ለሁለት ተሰንጥቃ ስለ ነበር መኮች ነብዩ (ﷺ) ጨረቃንም እንኳ ሳይቀር ደገመባት ስለ አሉ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከጨረቃ ምዕራፍ አንቀፅ (1-8) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. *ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤*
2. *የቂያማ ቀን ምልክቶች በጥቂቱም ቢሆን ማስታወስ፤*
3. *ስሜትን ማስታገስና መጠንቀቅ፤*
4. *ስሜቱን ለሚከተል ሁሉ ... ጥቅም እንደሌሌው፤*
5. *ከእነሱ በፊት የኑህ ነገድ አስተባበለች። ባሪያችንንም ኑህን አስተባበለ፤ እብደ ነውም አሉ። ተገለመጠም።*

٭ كَذَّبَتْ قَبْلَهُمْ قَوْمُ نُوحٍ فَكَذَّبُوا۟ عَبْدَنَا وَقَالُوا۟ مَجْنُونٌ وَٱزْدُجِرَ ﴿٩﴾ فَدَعَا رَبَّهُۥٓ أَنِّى
مَغْلُوبٌ فَٱنتَصِرْ ﴿١٠﴾ فَفَتَحْنَآ أَبْوَٰبَ ٱلسَّمَآءِ بِمَآءٍ مُّنْهَمِرٍ ﴿١١﴾ وَفَجَّرْنَا ٱلْأَرْضَ عُيُونًا
فَٱلْتَقَى ٱلْمَآءُ عَلَىٰٓ أَمْرٍ قَدْ قُدِرَ ﴿١٢﴾ وَحَمَلْنَٰهُ عَلَىٰ ذَاتِ أَلْوَٰحٍ وَدُسُرٍ ﴿١٣﴾ تَجْرِى بِأَعْيُنِنَا
جَزَآءً لِّمَن كَانَ كُفِرَ ﴿١٤﴾ وَلَقَد تَّرَكْنَٰهَآ ءَايَةً فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ ﴿١٥﴾ فَكَيْفَ كَانَ عَذَابِى
وَنُذُرِ ﴿١٦﴾ وَلَقَدْ يَسَّرْنَا ٱلْقُرْءَانَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ ﴿١٧﴾

**9-17.** ከእነርሱ በፊት የነብዩ ኑህ ነገድ አስተባበሉ። ባሪያችንንም ኑህን አስተባበሉ። ዕብድ ነውም አሉት። ተገላመጠም። ጌታውንም እኔ የተሸነፍኩ ነኝና እርዳኝ ሲል ተጣራ። ወዲውያ የሰማይን ደጃፎች በሚንቧቧ ውሃ ከፈትን። የምድርንም ምንጮች አፈነዳን። የሰማዩና የምድሩ ውሃውም ቀድሞ በተወሰነ ሁኔታ ላይ ተገናኘ። ባለ ብዙ ሳንቃዎችና ባለ ብዙ ሚስማሮች በሆነቸው ታንኳ ላይ ጫንነው። በጥበቃችን ስር ሆና ተንሻለለች። ተክዶ ለነበረው ሰው ምንዳ (ይህን ሰራን)። ተዐምር አድርገንም በእርግጥ ተውናት። ተገሳጭ ሰው አለን? ቅጣቴና ማስጠንቀቂያዎቼም እንዴት ነበሩ? ቁርኣንን ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው። ተገንዛቢ አለን?

ከጨረቃ ምዕራፍ (9) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት የመካ ሰዎች ነብዩ (ﷺ) ተዓምራቶችን እንዲያሳዩዋቸው ጠየቋቸው። እሳቸውም የጨረቃ ለሁለት መገመሰን ተዓምር አሳዩዋቸው።

كَذَّبَتْ عَادٌ فَكَيْفَ كَانَ عَذَابِى وَنُذُرِ ﴿١٨﴾ إِنَّآ أَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ رِيحًا صَرْصَرًا فِى يَوْمِ نَحْسٍ
مُّسْتَمِرٍّ ﴿١٩﴾ تَنزِعُ ٱلنَّاسَ كَأَنَّهُمْ أَعْجَازُ نَخْلٍ مُّنقَعِرٍ ﴿٢٠﴾

**18-20.** የዓድ ህዝቦች አስተባበሉ። ቅጣቴና ማስጠንቀቂያዎቼም እንዴት ነበሩ?፣ እኛ በእነርሱ ላይ ዘወትር መናጢ በሆነ ቀን በኃይል የምትንሻሻ ነፋስ ላክንባቸው። ሰዎችን ልክ ከስሮቻቸው የተጎለሰሱ የዘንባባ ግንዶች መስለው (ከተደበቁበት) ትነቅላቸዋለች።

فَكَيْفَ كَانَ عَذَابِي وَنُذُرِ ﴿٢١﴾ وَلَقَدْ يَسَّرْنَا ٱلْقُرْءَانَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ ﴿٢٢﴾

**21-22.** ቅጣቴና ማስጠንቀቂያዎቸም እንዴት ነበሩ? ቁርኣንንም ለማስታወስ በእርግጥ አገራነው ተገሳጭም አለን?

كَذَّبَتْ ثَمُودُ بِٱلنُّذُرِ ﴿٢٣﴾ فَقَالُوٓا۟ أَبَشَرًا مِّنَّا وَٰحِدًا نَّتَّبِعُهُۥٓ إِنَّآ إِذًا لَّفِى ضَلَٰلٍ وَسُعُرٍ ﴿٢٤﴾
أَءُلْقِىَ ٱلذِّكْرُ عَلَيْهِ مِنۢ بَيْنِنَا بَلْ هُوَ كَذَّابٌ أَشِرٌ ﴿٢٥﴾ سَيَعْلَمُونَ غَدًا مَّنِ ٱلْكَذَّابُ
ٱلْأَشِرُ ﴿٢٦﴾ إِنَّا مُرْسِلُوا۟ ٱلنَّاقَةِ فِتْنَةً لَّهُمْ فَٱرْتَقِبْهُمْ وَٱصْطَبِرْ ﴿٢٧﴾ وَنَبِّئْهُمْ أَنَّ ٱلْمَآءَ قِسْمَةٌۢ
بَيْنَهُمْ ۖ كُلُّ شِرْبٍ مُّحْتَضَرٌ ﴿٢٨﴾ فَنَادَوْا۟ صَاحِبَهُمْ فَتَعَاطَىٰ فَعَقَرَ ﴿٢٩﴾

**23-29.** የሰሙድ ህዝቦች በአስፈራሪዎቹ አስተባበሉ። ከእኛ የሆነን አንድን ሰው እንከተለዋለን? እኛ ያ ጌዜ በስህተትና በእብደት ውስጥ ነን አሉ። ከእኛ መካከል በእርሱ ላይ ብቻ ማስገንዘቢያ ራዕይ ተጣለለትን? አይደለም እርሱ ውሸታም ኩሩ ነው አሉ። ውሸታሙ ኩሩው ማን እንደሆነ ነገ በእርግጥ ያውቃሉ። እኛ ሴት ግመልን ለእነርሱ መፈተኛ ትሆን ዘንድ ላኪዎች ነን። ተጠባበቃቸውም ታገስም። ውሀውንም በመካከላቸው የተከፈለ መሆኑን ንገራቸው። ከውሃ የሆነ ፈንታ ሁሉ ተረኞቹ የሚጣዱት ነው። ጓደኞቻቸውንም ጠሩት። ወዲያውም (ሰይፉን) ተቀበለ። ወጋትም።

فَكَيْفَ كَانَ عَذَابِي وَنُذُرِ ﴿٣٠﴾ إِنَّآ أَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ صَيْحَةً وَٰحِدَةً فَكَانُوا۟ كَهَشِيمِ
ٱلْمُحْتَظِرِ ﴿٣١﴾ وَلَقَدْ يَسَّرْنَا ٱلْقُرْءَانَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ ﴿٣٢﴾

**30-32.** ቅጣቴንና ማስጠንቀቂያዎቼም እንዴት ነበሩ? እኛ ከእነርሱ ብቻ አንዲትን ጩኸት ላክንባቸው። ወዲያውም ከበረት አጣሪ (አጥር) እንደ ተሰባበረ እርግጋፊ ሆኑ። ቁርኣንን ለመገንዘብ አገራነው። ተገሳጭም አለን?

كَذَّبَتْ قَوْمُ لُوطٍۭ بِٱلنُّذُرِ ﴿٣٣﴾ إِنَّآ أَرْسَلْنَا عَلَيْهِمْ حَاصِبًا إِلَّآ ءَالَ لُوطٍۖ نَّجَّيْنَٰهُم بِسَحَرٍ ﴿٣٤﴾ نِّعْمَةً
مِّنْ عِندِنَاۚ كَذَٰلِكَ نَجْزِى مَن شَكَرَ ﴿٣٥﴾ وَلَقَدْ أَنذَرَهُم بَطْشَتَنَا فَتَمَارَوْا۟ بِٱلنُّذُرِ ﴿٣٦﴾ وَلَقَدْ
رَٰوَدُوهُ عَن ضَيْفِهِۦ فَطَمَسْنَآ أَعْيُنَهُمْ فَذُوقُوا۟ عَذَابِى وَنُذُرِ ﴿٣٧﴾ وَلَقَدْ صَبَّحَهُم بُكْرَةً عَذَابٌ
مُّسْتَقِرٌّ ﴿٣٨﴾ فَذُوقُوا۟ عَذَابِى وَنُذُرِ ﴿٣٩﴾ وَلَقَدْ يَسَّرْنَا ٱلْقُرْءَانَ لِلذِّكْرِ فَهَلْ مِن مُّدَّكِرٍ ﴿٤٠﴾

**33-40.** የሉጥ ህዝብ በአስፈራሪዎቹ አስተባበለች። እኛ በእነርሱ ላይ ጠጠርን ያዘለች ነፋስ ላክን። የሉጥ ቤተሰቦች ብቻ ሲቀሩ እነርሱንስ በሌሊት መጨረሻ ላይ አዳንናቸው። ከእኛ በሆነ ፀጋ አዳንናቸው። ልክ እንደዚሁ ያመሰገን ሰው እንመነዳለን። ብርቱ አያያዛችንን በእርግጥ አስጠነቀቅናቸው። በማስጠንቀቂያዎችም ተከራከሩ። እንግዶችንም እንዲያስመቻቸው ደጋግመው ፈለጉት። ወዲያውም ዓይኖቻቸውን አበስን። ቅጣቱንና ማስጠንቀቂያዎቹን ቅመሱ አልናቸው። በማለዳም ዘወታሪ የሆነ ቅጣት በእርግጥ ማለደባቸው። ቅጣቴንና ማስጠንቀቂያዎችም ቅመሱ ተባሉ። ቁርአንንም ለመገንዘብ በእርግጥ አገራነው። ተገሳጭም አለን?

وَلَقَدْ جَآءَ ءَالَ فِرْعَوْنَ ٱلنُّذُرُ ﴿٤١﴾ كَذَّبُوا۟ بِـَٔايَٰتِنَا كُلِّهَا فَأَخَذْنَٰهُمْ أَخْذَ عَزِيزٍ مُّقْتَدِرٍ ﴿٤٢﴾

**41-42.** የፈርዖንን ቤተሰቦች ማስጠንቀቂያዎች በእርግጥ መጡዋቸው። በታዐምራቶቻችንም በሁሏም አስተባበሉ። የብርቱ ቻይንም አያያዝ ያዝናቸው።

أَكُفَّارُكُمْ خَيْرٌ مِّنْ أُو۟لَٰٓئِكُمْ أَمْ لَكُم بَرَآءَةٌ فِى ٱلزُّبُرِ ﴿٤٣﴾ أَمْ يَقُولُونَ نَحْنُ جَمِيعٌ
مُّنتَصِرٌ ﴿٤٤﴾ سَيُهْزَمُ ٱلْجَمْعُ وَيُوَلُّونَ ٱلدُّبُرَ ﴿٤٥﴾ بَلِ ٱلسَّاعَةُ مَوْعِدُهُمْ وَٱلسَّاعَةُ أَدْهَىٰ
وَأَمَرُّ ﴿٤٦﴾ إِنَّ ٱلْمُجْرِمِينَ فِى ضَلَٰلٍ وَسُعُرٍ ﴿٤٧﴾ يَوْمَ يُسْحَبُونَ فِى ٱلنَّارِ عَلَىٰ وُجُوهِهِمْ ذُوقُوا۟
مَسَّ سَقَرَ ﴿٤٨﴾

**43-48.** ከሓዲያናችሁ ከእነዚያችሁ በላጮች ናቸውን? ወይንስ ለእናንተ በመጽሐፎች ውስጥ የተነገረ ነፃነት አልላችሁን? ወይስ እኛ የተረዳን ክምቹዎች ነን ይላሉ? ክምቹዎች በእርግጥ ድል ይመታሉ። ጀርባዎቻቸውንም ያዞራሉ። ይልቁንም ሰዓቲቱ ትንሳኤ ቀጠሮአቸው ናት። ሰዓቲቱም በጣም የከበደችና የመረረች ናት። አመፀኞች በስህተትና በእሳት ውስጥ ናቸው። በእሳት ውስጥ በፊታቸው በሚጎተትበት ቀን የሰቀርን (የጀሃነም ስም ነው) (ቅጣት) መንካት ቅመሱ ይባላሉ።

إِنَّا كُلَّ شَيۡءٍ خَلَقۡنَٰهُ بِقَدَرٖ ﴿٤٩﴾ وَمَآ أَمۡرُنَآ إِلَّا وَٰحِدَةٞ كَلَمۡحِۭ بِٱلۡبَصَرِ ﴿٥٠﴾
وَلَقَدۡ أَهۡلَكۡنَآ أَشۡيَاعَكُمۡ فَهَلۡ مِن مُّدَّكِرٖ ﴿٥١﴾ وَكُلُّ شَيۡءٖ فَعَلُوهُ فِي ٱلزُّبُرِ ﴿٥٢﴾
وَكُلُّ صَغِيرٖ وَكَبِيرٖ مُّسۡتَطَرٌ ﴿٥٣﴾

**49-53.** እኛ ሁሉን ነገር በልክ ፈጠርነው። ትዕዛዛችንም እንደ ዓይን ቅፅበት አንዲት ቃል እንጂ ሌላ አይደለም። ብጤዎቻችሁንም በእርግጥ አጠፋን ተገሳጭም አለን? የሰሩትም ነገር ሁሉ በመጽሐፎች ውስጥ ናቸው። ትንሹንም ትልቁም ሁሉ የተፃፈ ነው።

ከጨረቃ ምዕራፍ ከ (47-49) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- መኮች በቀድር እየተሟገቱ ከነብዩ (ﷺ) ጋር ሲጨቃጨቁ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው።

إِنَّ ٱلۡمُتَّقِينَ فِي جَنَّٰتٖ وَنَهَرٖ ﴿٥٤﴾ فِي مَقۡعَدِ صِدۡقٍ عِندَ مَلِيكٖ مُّقۡتَدِرِۭ ﴿٥٥﴾

**54-55.** አላህን ፈሪ የሆኑ ሰዎች በአትክልቶችና በወንዞች ውስጥ ናቸው። እነርሱም (ውድቅ ቃልና መውወንጀል በሌለበት) በእውነት መቀመጫ ውስጥ ላይ ከሆነው ንጉስ አላህ ዘንድ ናቸው።

**ከጨረቃ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-55) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ነብዩን (ﷺ) ማፅናናት፤
2. ቁረይሽን ማስጠንቀቅ፤
3. የኑህን ዘመን ማዕበል ማስታወስ፤
4. አላህ ለዚህ ኡማህ ቁርአንን መማርም ሆነ በእሱ መተግበሩ ማግራቱ፤
5. ግብረሰዶም የሰው ልጆች ከሚፈፅሟቸው እርኩስ ተግባሮች አንዱ መሆኑን፤
6. በዚህ ዓለም ላይ የሚፈፀሙት ሁሉ በአላህ ውሳኔ መሆኑን፤
7. አላህን የሚፈሩ ሁሉ በዱንያም በአኼራም ባለ ደስታዎች የሚሞናደሉ መሆናቸውን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የጨረቃ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (55)
# የአርረህማን ምዕራፍ
(ሱረቱ አር-ረህማን)

سُورَةُ الرَّحْمَٰنِ

**በመካ የወረደች ስትሆን። የምእራፉ አናቅፅ (78) ናቸው።**

## የሱረቱ አርረህማን መግቢያ

የአላህን ፀጋዎች በሰዎችም ሆነ ለጋኔኖች የዋለላቸው ውለታ አንድ በአንድ እያነሳ ሁሉን እንዲያስታውሱና እንዲያመሰግኑ ካስተማረ በኋላ በስተመጨረሻ አላህ ጥራት የሚገባው መሆኑን በማስገንዘብ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱلرَّحۡمَٰنُ ۝١ عَلَّمَ ٱلۡقُرۡءَانَ ۝٢ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ ۝٣ عَلَّمَهُ ٱلۡبَيَانَ ۝٤
ٱلشَّمۡسُ وَٱلۡقَمَرُ بِحُسۡبَانٖ ۝٥ وَٱلنَّجۡمُ وَٱلشَّجَرُ يَسۡجُدَانِ ۝٦

**1-6.** አልረህማን ቁርአንን አስተማረ።* ሰውን ፈጠረ። መናገርን አስተማረው። ፀሐይና ጨረቃ በተወሰነ (በየሂሳባቸው) ልክ ይሄዳሉ። የሰማይ ከዋክብትና የምድር ዛፎች ለእርሱ ይሰግዳሉ።

* መኮች አረህማን ምንድነው ብለው ሲጠየቁ ነው የወረደው የሚሉ የተፍሲር ምሁራን እንዳሉ ሁሉ ሌሎች ደግሞ መኮች ነብዩን የሚያስተምራቸው ሰው ነው ባሉ ጊዜ ነው የወረደው ያሉም አሉ።

وَٱلسَّمَآءَ رَفَعَهَا وَوَضَعَ ٱلۡمِيزَانَ ۝٧ أَلَّا تَطۡغَوۡاْ فِي ٱلۡمِيزَانِ ۝٨
وَأَقِيمُواْ ٱلۡوَزۡنَ بِٱلۡقِسۡطِ وَلَا تُخۡسِرُواْ ٱلۡمِيزَانَ ۝٩

**7-9.** ሰማይንም ከፍ አደረጋት። የትክክለኛነትን ሚዛንንም አስቀመጠ። በሚዛን ስትመዘኑ እንዳትበድሉ። መመዘንንም በትክክል መዝኑ። ስትመዝኑም አታጉድሉ።

وَٱلۡأَرۡضَ وَضَعَهَا لِلۡأَنَامِ ۝١٠ فِيهَا فَٰكِهَةٞ وَٱلنَّخۡلُ ذَاتُ ٱلۡأَكۡمَامِ ۝١١
وَٱلۡحَبُّ ذُو ٱلۡعَصۡفِ وَٱلرَّيۡحَانُ ۝١٢ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ۝١٣

**10-13.** ምድርንም ለፍጡር አደላደላት። በውስጧ እሸት ባለ ሽፍን የሆኑ ዘንባባዎችም ያሉባት ስትሆን። የገለባ ባለቤት የሆነ ቅንጣትም ባለ መልካም መዓዛ ቅጠሎችም ያሉባት ስትሆን። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች መካከል በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

خَلَقَ ٱلْإِنسَـٰنَ مِن صَلْصَـٰلٍ كَٱلْفَخَّارِ ﴿١٤﴾ وَخَلَقَ ٱلْجَآنَّ مِن مَّارِجٍ مِّن نَّارٍ ﴿١٥﴾
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿١٦﴾

**14-16.** ሰውን እንደ ሸክላ ከሚቅጨለጨል ደረቅ ጭቃ ፈጠረው። ጃንንም ከእሳት ከሆነ ነበልባል ፈጠረው። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

رَبُّ ٱلْمَشْرِقَيْنِ وَرَبُّ ٱلْمَغْرِبَيْنِ ﴿١٧﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿١٨﴾

**17-18.** የሁለቱ ምስራቆችና የሁለቱ ምዕራቦች* ጌታ ነው። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

* የሁለቱ ያለበት ምክኒያት የበጋና የክርምቱን መውጫና መግቢያ በማየት ነው።

مَرَجَ ٱلْبَحْرَيْنِ يَلْتَقِيَانِ ﴿١٩﴾ بَيْنَهُمَا بَرْزَخٌ لَّا يَبْغِيَانِ ﴿٢٠﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٢١﴾

**19-21.** ሁለቱም ባህሮች የሚገናኙ ሲሆኑ ለቀቃቸው። እንዳይዋሀዱ በመካከላቸው የማይታይ መጋረጃ አለ። አንዱ በሌላው ላይ ወሰን አያልፉም*። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

* የጂረት ወንዞች በባህሮች ላይ እንዲፈሱ ያደረገና የባህሩ ጨዋማነት በጂረት ውሃው ላይ ለውጥ እንዳያመጣ ውስጣዊ መጋረጃን ያደረገ ማለት ነው።

يَخْرُجُ مِنْهُمَا ٱللُّؤْلُؤُ وَٱلْمَرْجَانُ ﴿٢٢﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٢٣﴾

**22-23.** ሉልና መርጃን የተባሉት ማዕድኖች ከሁለቱ ባህሮች ይወጣሉ። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

وَلَهُ ٱلْجَوَارِ ٱلْمُنشَـَٔاتُ فِى ٱلْبَحْرِ كَٱلْأَعْلَـٰمِ ﴿٢٤﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٢٥﴾

**24-25.** እንደ ጋራዎች ሆነው በባህር ውስጥ የተሰሩት ተንሻላዩችም ታንኳዎች የእርሱ ናቸው። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

كُلُّ مَنۡ عَلَيۡهَا فَانٖ ٢٦ وَيَبۡقَىٰ وَجۡهُ رَبِّكَ ذُو ٱلۡجَلَٰلِ وَٱلۡإِكۡرَامِ ٢٧
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ٢٨

**26-28.** በእርሷ (በምድር) ላይ ያለው ሁሉ ጠፊ ነው፡፡ የልቅና እና የልግስና ባለቤት የሆነው የጌታህ ፊትም ይቀራል (አይጠፋም)፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

يَسۡـَٔلُهُۥ مَن فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۚ كُلَّ يَوۡمٍ هُوَ فِي شَأۡنٖ ٢٩
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ٣٠

**29-30.** በሰማያትና በምድር ውስጥ ያሉት ሁሉ ይለምኑታል በየቀኑ ሁሉ እርሱ በስራ ላይ ነው፡፡ (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

سَنَفۡرُغُ لَكُمۡ أَيُّهَ ٱلثَّقَلَانِ ٣١ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ٣٢

**31-32.** እናንተ ሁለት ከባዶች ሰዎችንና ጋኔኖች ሆይ! ለእናንተ መቆጣጠር በእርግጥ እናስባለን፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ፣ ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

يَٰمَعۡشَرَ ٱلۡجِنِّ وَٱلۡإِنسِ إِنِ ٱسۡتَطَعۡتُمۡ أَن تَنفُذُواْ مِنۡ أَقۡطَارِ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ فَٱنفُذُواْۚ
لَا تَنفُذُونَ إِلَّا بِسُلۡطَٰنٖ ٣٣ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ٣٤

**33-34.** የአጋንንትና የሰው ጭፍሮች ሆይ! ከሰማያትና ከምድር ቀበሌዎች መውጣትን ከቻላችሁ ውጡ፡፡ በስልጣን እንጂ አትወጡም፡፡ (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

يُرۡسَلُ عَلَيۡكُمَا شُوَاظٞ مِّن نَّارٖ وَنُحَاسٞ فَلَا تَنتَصِرَانِ ٣٥
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ٣٦

**35-36.** በሁለታችሁም ላይ ከእሳት ነበላባልና ጭስም ይላክባችኋል፡፡ ሁለታችሁም ድል አታደርጉም፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

فَإِذَا ٱنشَقَّتِ ٱلسَّمَآءُ فَكَانَتْ وَرْدَةً كَٱلدِّهَانِ ﴿٣٧﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٣٨﴾

**37-38.** ሰማይ በተሰነጠቀችና እንደፅጌረዳ እንደታረበ ቆዳ በሆነች ጊዜ (ጭንቁን ምን አበረታው)። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ፣ ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

فَيَوْمَئِذٍ لَّا يُسْـَٔلُ عَن ذَنۢبِهِۦٓ إِنسٌ وَلَا جَآنٌّ ﴿٣٩﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٤٠﴾

**39-40.** በዚያም ቀን ሰውም ጀኝንም ከሀጢአቱ አይጠየቅም። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

يُعْرَفُ ٱلْمُجْرِمُونَ بِسِيمَٰهُمْ فَيُؤْخَذُ بِٱلنَّوَٰصِى وَٱلْأَقْدَامِ ﴿٤١﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٤٢﴾

**41-42.** ከሓዲያን በምልክታቸው ይታወቃሉ። ከዚያ አናቶቻቸውንና እግሮቻቸውን ይያዛሉ። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

هَٰذِهِۦ جَهَنَّمُ ٱلَّتِى يُكَذِّبُ بِهَا ٱلْمُجْرِمُونَ ﴿٤٣﴾ يَطُوفُونَ بَيْنَهَا وَبَيْنَ حَمِيمٍ ءَانٍ ﴿٤٤﴾
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٤٥﴾

**43-45.** ይህች ያቺ አመፀኞች በእርሷ ያስተባሉባት የነበረችው ገሀነም ናት ይባላሉ። በእርሷና በጣም ሞቃት በሆነ ፍል ውሃ መካከል ይመላለሳሉ። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

وَلِمَنْ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ جَنَّتَانِ ﴿٤٦﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٤٧﴾

**46-47.** (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታውም ፊት መቆምን ለፈራ ሰው ሁለት ገነቶች አሉት፡ (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

ذَوَاتَآ أَفْنَانٍ ﴿٤٨﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٤٩﴾

**48-49.** የቀንዘሎች ባለቤቶች የሆኑ ገነቶች አሉ። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

فِيهِمَا عَيْنَانِ تَجْرِيَانِ ﴿٥٠﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٥١﴾

**50-51.** በሁለቱ ውስጥ የሚፈሱ ሁለት ምንጮች አሉ። (ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ!) ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

فِيهِمَا مِن كُلِّ فَٰكِهَةٖ زَوۡجَانِ ﴿٥٢﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٥٣﴾

**52-53.** በሁለቱ ውስጥ ከፍራፍሬዎች ሁሉ ሁለት ዓይነቶች (እርጥብና ደረቅ) አሉ። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

مُتَّكِـِٔينَ عَلَىٰ فُرُشِۭ بَطَآئِنُهَا مِنۡ إِسۡتَبۡرَقٖۚ وَجَنَى ٱلۡجَنَّتَيۡنِ دَانٖ ﴿٥٤﴾
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٥٥﴾

**54-55.** የውስጥ ጉስጉሳቸው ከወፍራም ሀር በሆኑ ምንጣፎች ላይ የተመቻቹ ሲሆን ይንፈላሰሳሉ፤ የሁለቱም ገነቶች ፍሬ ለለቃሚ ቅርብ ነው። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባብላላችሁ?

فِيهِنَّ قَٰصِرَٰتُ ٱلطَّرۡفِ لَمۡ يَطۡمِثۡهُنَّ إِنسٞ قَبۡلَهُمۡ وَلَا جَآنّٞ ﴿٥٦﴾
فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٥٧﴾

**56-57.** በውስጣቸው ከባሎቻቸው በፊት ሰውም ጃንም ያልገሰሳቸው ዓይኖቻቸውን (በባሎቻቸው ላይ ብቻ) አሳጣሪዎች ሴቶች አሉ። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

كَأَنَّهُنَّ ٱلۡيَاقُوتُ وَٱلۡمَرۡجَانُ ﴿٥٨﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٥٩﴾

**58-59.** (ቁንጅናቸው) ልክ የያቁትንና የመርጃንን ማዕድኖች ይመስላሉ። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

هَلۡ جَزَآءُ ٱلۡإِحۡسَٰنِ إِلَّا ٱلۡإِحۡسَٰنُ ﴿٦٠﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٦١﴾

**60-61.** የበጎ ስራ ዋጋ በጎ እንጂ ሌላ ነውን? ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ፣ ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

وَمِن دُونِهِمَا جَنَّتَانِ ﴿٦٢﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٦٣﴾

**62-63.** ከሁለት ገነቶች ሌላ ሁለት ገነቶች አሉ። ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

مُدۡهَآمَّتَانِ ﴿٦٤﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٦٥﴾

64-65. ከልምላሜዎቻቸው የተነሳ ወደ ጥቁረት ያዘነበሉ ናቸው፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

فِيهِمَا عَيۡنَانِ نَضَّاخَتَانِ ﴿٦٦﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٦٧﴾

66-67. በውስጣቸው ሁለት የሚንፏፉ ምንጮች አሉ፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

فِيهِمَا فَٰكِهَةٞ وَنَخۡلٞ وَرُمَّانٞ ﴿٦٨﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٦٩﴾

68-69. በውስጣቸው ፍራፍሬ ዘንባባና ሩማንም አለ፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

فِيهِنَّ خَيۡرَٰتٌ حِسَانٞ ﴿٧٠﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٧١﴾

70-71. በውስጣቸው ፀባየ መልካሞችና መልከ ውብ ሴቶች አሉ፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

حُورٞ مَّقۡصُورَٰتٞ فِي ٱلۡخِيَامِ ﴿٧٢﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٧٣﴾

72-73. በድንኳኖች ውስጥ የተጨጎሉ የዓይኖቻቸው ጥቁረትና ንጣት ደማቅ የሆኑ ናቸው፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ፣ ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

لَمۡ يَطۡمِثۡهُنَّ إِنسٞ قَبۡلَهُمۡ وَلَا جَآنّٞ ﴿٧٤﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٧٥﴾

74-75. ከእነርሱ በፊት ሰውም ሆነ ጃን አልገሰሳቸውም፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ፣ ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

مُتَّكِـِٔينَ عَلَىٰ رَفۡرَفٍ خُضۡرٖ وَعَبۡقَرِيٍّ حِسَانٖ ﴿٧٦﴾ فَبِأَيِّ ءَالَآءِ رَبِّكُمَا تُكَذِّبَانِ ﴿٧٧﴾

76-77. በሚያረገርጉ አረንጓዴ ምንጣፎችና በሚያምሩ ስጋጃዎች ላይ የተደላደሉ ሲሆኑ ይቀመጣሉ፡፡ ሰዎችና ጋኔኖች ሆይ! ከጌታችሁ ፀጋዎች በየትኛው ታስተባላላችሁ?

تَبَٰرَكَ ٱسۡمُ رَبِّكَ ذِي ٱلۡجَلَٰلِ وَٱلۡإِكۡرَامِ ﴿٧٨﴾

78. የግርማ የመከበር ባለቤት የሆነው ጌታህ ስም ተባረከ፡፡

**ከአር-ረህማን ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-78) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አልረህማን የሚለው የአላህ ስም ከእሱ ሌላ ማንም ሊሰየምበት እንደማይችል፤
2. እውነትን መቀበልና በእሱ ዙሪያ በየትኛውም ጉዳይ አለማስተባበል፤
3. ከአላህ ፀጋዎች በየትኛውም አላስተባብልም ማለቱ ተገቢ መሆኑን፤
4. የስነፈለክ ትምህርትን በተገቢው መማር፤
5. የሰው ልጅና የጋኔን አፈጣጠር መግለፅ፤
6. የፀሐይ መውጫዎችና መግቢያዎችን ማወቅ፤
7. የያቁትና የመርጃን ማዕድናትን መጠቀም፤
8. አላህን ቁጥር ስፍር በሌለው ፀጋው ማመስገን፤
9. ሙቶ መነሳትን እውነትነት ማረጋገጥ፤
10. የአላህን ኃያልነትና ልዕልና መቀበል፤
11. አላህን በሁሉም ሰዓት ማመስገን ማወደስ ተገቢ ስለመሆኑ፤
12. የዓለምን መፈራረስ ታሪክ ማስታወስ፤
13. ሰዎች ከየቀብራቸው እንደሚቀሰቀሱ፤
14. ወንጀሎችን ማውገዝ፤
15. አላህን መፍራት ያለው ክብር፤
16. የጀነት ሴቶች ክብር እንደሆኑ፤
17. ትልቅ ሴቶች ማለት አይንዋን በባሏ ላይ ያሰጠረች መሆንዋን፤
18. ጋኔንም ልክ እንደ ሰዎች ሁሉ በስራቸው መሰረት ጀነት እንደሚገባ፤
19. የአኼራ ፀጋና ደስታ ከዱንያ ደስታና ፌስታ እንደሚበልጥ በይፋ ማወጅ፤
20. የተምር፤ ሩማን ቅጠሎች ከፍተኛ ጥቅም እንዳላቸው፤
21. በቤቷ የምትቀመጥ ሴት በአላህ ዘንድ ያላቸው ክብር፤
22. ጅኖችም ጀነት እንደሚገቡ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የአረሀረማን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

ምዕራፍ (56)
# የመከራይቱ ምዕራፍ
(ሱረቱ አል-ዋቂዐህ)

سُورَةُ الوَاقِعَةِ

**የወረደው በመካ ነው። የአንቀፁ ብዛት (96) ናቸው።**

## የሱረቱ አል ዋቂዓህ መግቢያ

ስለቂያማ መምጣትና ከእሱም ጋር የተያያዙ ነገሮችን በማውሳት ትምህርቱን ይጀምራል። ከዚያ ሰዎች በዚያን ዕለት 3 ክፍሎች እንደሚሆኑና እያንዳንዳቸው ምን እንደሆኑ በዝርዝር አስቀምጦ ደረጃውም እንደሁኔታው በወንጀላቸውና በኸይር ስራቸው ልክ እንደሚሆን ያስረዳል። ከዚያ በመቀጠል የአላህን ፀጋዎች የሚያሳዩትን ውሃ፣ አዝርዕት፣ እሳት በማንሳት የአላህን ኃያልነት በዚህ እንኳን ሊገነዘቡ አለመቻላቸውን ይወቅሳል። በስተመጨረሻም በዚሁ ምዕራፍ ውስጥ የተጠቀሱ ነገሮች ሁሉ እውነትና ሐቅ መሆናቸውን በመደንገግ ነው መልዕክቱን የሚያጠቃልለው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِذَا وَقَعَتِ ٱلۡوَاقِعَةُ ﴿١﴾ لَيۡسَ لِوَقۡعَتِهَا كَاذِبَةٌ ﴿٢﴾ خَافِضَةٞ رَّافِعَةٌ ﴿٣﴾
إِذَا رُجَّتِ ٱلۡأَرۡضُ رَجّٗا ﴿٤﴾ وَبُسَّتِ ٱلۡجِبَالُ بَسّٗا ﴿٥﴾ فَكَانَتۡ هَبَآءٗ مُّنۢبَثّٗا ﴿٦﴾

**1-6.** *መከራይቱ (ቂያማ) በወደቀች ጊዜ። (ቂያማ) ለመውደቋ አስተባባይ አንዲትም ነፍስ የለችም። እርሷ (የሳት ሰወችን) ዝቅ አድራጊና (የጀነት ሰዎችን) ደግሞ ከፍ አድራጊ ናት። ምድር መናወጥን በተናወጠች ጊዜ። ተራራዎች (እንደተፈጨ ዱቄት በሆኑ ጊዜ) መፈርፈርን በተፈረፈሩ ጊዜ። ከዚያ የተበተነ ብናኝ በሆኑ ጊዜ።

* ቲርሚዚ በዘገቡት ሀዲስ አቡበክር ሲዲቅ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሸበቱ ብለው ሲጠይቋቸው ይህ ና መሰሎቹ እንዳሸበቷቸው ተናግረዋል።

وَكُنتُمۡ أَزۡوَٰجٗا ثَلَٰثَةٗ ﴿٧﴾ فَأَصۡحَٰبُ ٱلۡمَيۡمَنَةِ مَآ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَيۡمَنَةِ ﴿٨﴾
وَأَصۡحَٰبُ ٱلۡمَشۡـَٔمَةِ مَآ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَشۡـَٔمَةِ ﴿٩﴾ وَٱلسَّٰبِقُونَ ٱلسَّٰبِقُونَ ﴿١٠﴾
أُوْلَٰٓئِكَ ٱلۡمُقَرَّبُونَ ﴿١١﴾ فِي جَنَّٰتِ ٱلنَّعِيمِ ﴿١٢﴾

**7-12.** እናንተ ሰዎች ሶስት ዓይነቶችም በሆናችሁ ጊዜ (የሳት ሰወችን) ዝቅ እና (የጀነት ሰዎችን) ከፍ (ታደርጋለች)። እናም በዚያ ቀን የቀኝ ጓዶች ለመሆን የበቁ ሁሉ ምን (የተከበሩ) የቀኝ ጓዶች ናቸው። የግራ ጓዶች ምን (የተዋረዱ)

የግራ ጓዶች ናቸው። እነዚያ (ለበጎ ስራ) ቀዳሚዎች የሆኑ ሁሉ (ለገነትም) ቀዳሚዎች ናቸው። እነዚያ በአላህ ዘንድም። በመደሰቻ ገነቶች ውስጥ ሲሆኑ ባለሟሎች ናቸው።

ثُلَّةٌ مِّنَ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿١٣﴾ وَقَلِيلٌ مِّنَ ٱلۡأٓخِرِينَ ﴿١٤﴾ عَلَىٰ سُرُرٍ مَّوۡضُونَةٍ ﴿١٥﴾ مُّتَّكِـِٔينَ عَلَيۡهَا مُتَقَٰبِلِينَ ﴿١٦﴾ يَطُوفُ عَلَيۡهِمۡ وِلۡدَٰنٌ مُّخَلَّدُونَ ﴿١٧﴾ بِأَكۡوَابٍ وَأَبَارِيقَ وَكَأۡسٍ مِّن مَّعِينٍ ﴿١٨﴾ لَّا يُصَدَّعُونَ عَنۡهَا وَلَا يُنزِفُونَ ﴿١٩﴾ وَفَٰكِهَةٍ مِّمَّا يَتَخَيَّرُونَ ﴿٢٠﴾ وَلَحۡمِ طَيۡرٍ مِّمَّا يَشۡتَهُونَ ﴿٢١﴾ وَحُورٌ عِينٌ ﴿٢٢﴾ كَأَمۡثَٰلِ ٱللُّؤۡلُوِ ٱلۡمَكۡنُونِ ﴿٢٣﴾ جَزَآءَۢ بِمَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ﴿٢٤﴾ لَا يَسۡمَعُونَ فِيهَا لَغۡوًا وَلَا تَأۡثِيمًا ﴿٢٥﴾ إِلَّا قِيلٗا سَلَٰمٗا سَلَٰمٗا ﴿٢٦﴾

**13-26.** (የዚህ እድል ባለ ቤቶች) ከፊተኞቹ ብዙ ቡድኖች ናቸው። ከኋለኞቹ ግን ጥቂቶች ናቸው። በተታቱ አልጋዎች ላይ ይሆናሉ። በእርሷ ላይ የተመቻቹና ፊት ለፊት የተቅጣጩ ሲሆኑ። ለእነርሱ (ለማገለገል) በእነርሱ ዙሪያ ሁልጊዜ የማያረጁ ወጣት ልጆች ይዘዋወራሉ። ከጠጅ ምንጭ በብርጭቆዎችና በኩስኩስቶች በፅዋም (በእነርሱ ዙሪያ ይዝዞራሉ)። ከእርሷ የራስ ምታት እንኳን አያገኛቸውም። አይሰክሩምም። እነዚያ ወጣት ልጆች ከእሸቶች ከሚመርጡት ዓይነት ከሚፈልጉት የበራሪ ስጋ ይዘው (ይዞሩላቸዋል)። ዓይናማዎች የሆኑ ነጫጭ ቆንጆ ሴቶችም አሏቸው። ልክ እንደተሸፈነ ሉል የሚመስሉ። በዚያ ይሰሩት በነበሩት መልካም ተግባር ምክንያት ዋጋ ይሆን ዘንድ (ይህንን አደርግንላቸው)። በውስጧ ውድቅ ንግግርንና መውወንጀል አይሰሙም። ሰላም መባባልን ግን ይሰማሉ።

وَأَصۡحَٰبُ ٱلۡيَمِينِ مَآ أَصۡحَٰبُ ٱلۡيَمِينِ ﴿٢٧﴾ فِي سِدۡرٍ مَّخۡضُودٍ ﴿٢٨﴾ وَطَلۡحٍ مَّنضُودٍ ﴿٢٩﴾ وَظِلٍّ مَّمۡدُودٍ ﴿٣٠﴾ وَمَآءٍ مَّسۡكُوبٍ ﴿٣١﴾ وَفَٰكِهَةٍ كَثِيرَةٍ ﴿٣٢﴾ لَّا مَقۡطُوعَةٍ وَلَا مَمۡنُوعَةٍ ﴿٣٣﴾ وَفُرُشٍ مَّرۡفُوعَةٍ ﴿٣٤﴾ إِنَّآ أَنشَأۡنَٰهُنَّ إِنشَآءً ﴿٣٥﴾ فَجَعَلۡنَٰهُنَّ أَبۡكَارًا ﴿٣٦﴾ عُرُبًا أَتۡرَابًا ﴿٣٧﴾ لِّأَصۡحَٰبِ ٱلۡيَمِينِ ﴿٣٨﴾ ثُلَّةٌ مِّنَ ٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٣٩﴾ وَثُلَّةٌ مِّنَ ٱلۡأٓخِرِينَ ﴿٤٠﴾

**27-40.** የቀኝ ጓዶች ምንኛ የከበሩ የቀኝ ጓዶች ናቸው። በተቀፈቀፈ (እሾህ በሌለው) ቁርቁራ ውስጥ ናቸው። ፍሬው በተነባበረ ሙዝ ዛፍም ውስጥ። በተዘረጋ ጥላ ስርም ናቸው። በሚንቧቧ ውሃ አጠገብም ናቸው። በዓይነት ብዙ (አይነት) ፍራፍሬዎችም የማትቋረጥም፤ የማትከለከል የሆነች ከፍ በተደረጉ

ምንጣፎችም ሴቶችም መካከል ናቸው። እኛ (የጀነት ሴቶችን) አዲስ ፍጥረት አድርገን ፈጠርናቸው። እናም ደናግሎችም አደረግናቸው። ለባሎቻቸው ተሽሞርሟሪዎችና እኩያዎች አደረግናቸው። ለቀኝ ጓዶች አዘጋጀናቸው። ከፊተኞቹ ብዙ ቡድኖች ናቸው። ከኋለኞቹም ብዙ ቡድኖች ናቸው።

وَأَصۡحَٰبُ ٱلشِّمَالِ مَآ أَصۡحَٰبُ ٱلشِّمَالِ ﴿٤١﴾ فِي سَمُومٖ وَحَمِيمٖ ﴿٤٢﴾ وَظِلّٖ مِّن يَحۡمُومٖ ﴿٤٣﴾
لَّا بَارِدٖ وَلَا كَرِيمٍ ﴿٤٤﴾ إِنَّهُمۡ كَانُواْ قَبۡلَ ذَٰلِكَ مُتۡرَفِينَ ﴿٤٥﴾ وَكَانُواْ يُصِرُّونَ عَلَى ٱلۡحِنثِ
ٱلۡعَظِيمِ ﴿٤٦﴾ وَكَانُواْ يَقُولُونَ أَئِذَا مِتۡنَا وَكُنَّا تُرَابٗا وَعِظَٰمًا أَءِنَّا لَمَبۡعُوثُونَ ﴿٤٧﴾ أَوَءَابَآؤُنَا
ٱلۡأَوَّلُونَ ﴿٤٨﴾ قُلۡ إِنَّ ٱلۡأَوَّلِينَ وَٱلۡأٓخِرِينَ ﴿٤٩﴾ لَمَجۡمُوعُونَ إِلَىٰ مِيقَٰتِ يَوۡمٖ مَّعۡلُومٖ ﴿٥٠﴾ ثُمَّ إِنَّكُمۡ
أَيُّهَا ٱلضَّآلُّونَ ٱلۡمُكَذِّبُونَ ﴿٥١﴾ لَأٓكِلُونَ مِن شَجَرٖ مِّن زَقُّومٖ ﴿٥٢﴾ فَمَالِـُٔونَ مِنۡهَا ٱلۡبُطُونَ ﴿٥٣﴾
فَشَٰرِبُونَ عَلَيۡهِ مِنَ ٱلۡحَمِيمِ ﴿٥٤﴾ فَشَٰرِبُونَ شُرۡبَ ٱلۡهِيمِ ﴿٥٥﴾ هَٰذَا نُزُلُهُمۡ يَوۡمَ ٱلدِّينِ ﴿٥٦﴾

**41-56.** የግራ ጓዶችም ምንኛ (የተዋረዱ)።* የግራ ጓዶች ናቸው። በመርዛም ነፋስና በጣም በፈላ ውሃም ውስጥ ናቸው። ከጥቁር ጭስም በሆነ ጥላ ውስጥ ቀዝቃዛ መልካም ያልሆነ፤ እነርሱ ከዚህ በፊት የነብያትን አስተምህሮት ወደ ጎን የተው የዱንያ ቅምጥሎች ነበሩና። በታላቅ ኃጢአትም ላይ ይዘወትሩ ነበሩና። ሞትን አፈር አጥንቶችም በሆን ጊዜ እኛ የምንቀሰቀስ ነን? ይሉም ነበሩና ነው። የፊተኞቹ አባቶቻችንንም? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ፊተኞቹም ሆኑ ኋለኞቹ በተወሰነ ቀን ቀጠሮ በእርግጥ ተሰብሳቢዎች ናቸው በላቸው። ከዚያ እናንተ (ጠማሞችና አስተባባዩች ሆይ!) ከዘቁም ዛፍ በእርግጥ በይዎች ናችሁ። ከእርሷም ሆዶቻችሁን ሞይዎች ናችሁ። በእርሱም ላይም ከፈላ ውሃ ጠጪዎች ናችው። የተጠሙንም ግመሎች አጠጣጥ ብጤ ጠጪዎች ናቸው። ይህ በፍርዱ ቀን መስተንግዷቸው ነው።

* ዉዱእ የሌለው ሰው ቁርኣንን መንካት ይችላል ወይስ አይቺልም በማለት የተፈጠረው ክርክር የዚህን የቁርኣን አንቀፅ መልዕክት መነሻ አድርጎ ነው። የክርክሩ አይነትም ለሁለት ይከፈላል:-

(ሀ) ንፁህ የተባሉት መላይኮች ወይስ ሰዎች የሚለው ሲሆን፤

(ለ) አባባሉ ራሱ ከልካይ ነው ወይስ ዘገባ አቅራቢ የሚሉት ናቸው። እነዚህን መሰረት አድርጎ የተካሄደው ክርክር ንፁህ ማለት ሰዎች ማለት ነው አባባሉም ከልካይ ነው ብለው የተረዱ ክፍሎች ያለ ዉዱዕ ቁርኣንን መንካት ሲከለክሉ፤ ሌሎቹ ግን ምንም ችግር የለበትም ብለዋል።

نَحۡنُ خَلَقۡنَٰكُمۡ فَلَوۡلَا تُصَدِّقُونَ ﴿٥٧﴾

**57.** (ሰዎች ሆይ!) እኛ ፈጠርናችሁ አታምኑምን?

أَفَرَءَيْتُم مَّا تُمْنُونَ ﴿٥٨﴾ ءَأَنتُمْ تَخْلُقُونَهُۥٓ أَمْ نَحْنُ ٱلْخَـٰلِقُونَ ﴿٥٩﴾ نَحْنُ قَدَّرْنَا بَيْنَكُمُ ٱلْمَوْتَ
وَمَا نَحْنُ بِمَسْبُوقِينَ ﴿٦٠﴾ عَلَىٰٓ أَن نُّبَدِّلَ أَمْثَـٰلَكُمْ وَنُنشِئَكُمْ فِى مَا لَا تَعْلَمُونَ ﴿٦١﴾ وَلَقَدْ
عَلِمْتُمُ ٱلنَّشْأَةَ ٱلْأُولَىٰ فَلَوْلَا تَذَكَّرُونَ ﴿٦٢﴾

58-62. በሴቶች ማህፀኖች የምታፈሱትን (የምትረጩትን) ፍቶት አያችሁን? እናንተ ትፈጥሩታላችሁን! ወይስ እኛ ነን ፈጣሪዎቹ? እኛ ሞትን (ጊዜውን) በመካከላችሁ ወሰንን እኛም ተሸናፊዎች አይደለንም። ብጤዎቻችሁም በመለወጥና በዚያ በማታውቁትም ቅርፅ እናንተኑ በመፍጠር ላይ አንሸነፍም። የፊተኛይቱን አፈጣጠር በእርግጥ አውቃችኋል አትገነዘቡምን?

أَفَرَءَيْتُم مَّا تَحْرُثُونَ ﴿٦٣﴾ ءَأَنتُمْ تَزْرَعُونَهُۥٓ أَمْ نَحْنُ ٱلزَّٰرِعُونَ ﴿٦٤﴾ لَوْ نَشَآءُ لَجَعَلْنَـٰهُ حُطَـٰمًا
فَظَلْتُمْ تَفَكَّهُونَ ﴿٦٥﴾ إِنَّا لَمُغْرَمُونَ ﴿٦٦﴾ بَلْ نَحْنُ مَحْرُومُونَ ﴿٦٧﴾

63-67. የምትዘሩትን አዝርእት አያችሁን? እናንተ ታበቅሉታላችሁን? ወይስ እኛ አብቃዮቹ ነን? ብንሻ ኖሮ ደረቅ ስብርብር ባረደግነው እና የምትደነቁም በሆናችሁ ነበር። እኛ በእዳ ተያዥዎች ነን። በእርግጥም እኛ (ከመጠቀም) የተከለከልን ነን ትሉ ነበር።

أَفَرَءَيْتُمُ ٱلْمَآءَ ٱلَّذِى تَشْرَبُونَ ﴿٦٨﴾ ءَأَنتُمْ أَنزَلْتُمُوهُ مِنَ ٱلْمُزْنِ أَمْ نَحْنُ ٱلْمُنزِلُونَ ﴿٦٩﴾
لَوْ نَشَآءُ جَعَلْنَـٰهُ أُجَاجًا فَلَوْلَا تَشْكُرُونَ ﴿٧٠﴾

68-70. ያንን ምትጠጡትን ውሃ አያችሁን? እናንተ ከደመናው አወረዳችሁትን? ወይስ እኛ አውራጆቹ ነን? ብንፈልግ ኖሮ መርጋጋ ባደረግነው ነበር። አታመሰግኑምን?

أَفَرَءَيْتُمُ ٱلنَّارَ ٱلَّتِى تُورُونَ ﴿٧١﴾ ءَأَنتُمْ أَنشَأْتُمْ شَجَرَتَهَآ أَمْ نَحْنُ ٱلْمُنشِـُٔونَ ﴿٧٢﴾
نَحْنُ جَعَلْنَـٰهَا تَذْكِرَةً وَمَتَـٰعًا لِّلْمُقْوِينَ ﴿٧٣﴾

71-73. ያችንም የምትሰብቋት እሳት አያችሁን? እናንተ ዛፏን ፈጠራችሁን? ወይስ እኛ ፈጣሪዎች ነን? እኛ ለገሀነም ማስታወሻ ለመንገደኞችም መጠቀሚያ አደረግናት።

فَسَبِّحْ بِٱسْمِ رَبِّكَ ٱلْعَظِيمِ ﴿٧٤﴾

74. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የታላቁን ጌታህንም ስም አጥራው።

۞ فَلَآ أُقۡسِمُ بِمَوَٰقِعِ ٱلنُّجُومِ ٧٥ وَإِنَّهُۥ لَقَسَمٞ لَّوۡ تَعۡلَمُونَ عَظِيمٌ ٧٦ إِنَّهُۥ لَقُرۡءَانٞ
كَرِيمٞ ٧٧ فِي كِتَٰبٖ مَّكۡنُونٖ ٧٨ لَّا يَمَسُّهُۥٓ إِلَّا ٱلۡمُطَهَّرُونَ ٧٩ تَنزِيلٞ مِّن رَّبِّ
ٱلۡعَٰلَمِينَ ٨٠ أَفَبِهَٰذَا ٱلۡحَدِيثِ أَنتُم مُّدۡهِنُونَ ٨١ وَتَجۡعَلُونَ رِزۡقَكُمۡ أَنَّكُمۡ
تُكَذِّبُونَ ٨٢

75-82. በከዋክብትም መጥለቂያዎች እምላለሁ። እርሱን ብታውቁ ታላቅ መሀላ ነው። እርሱ የተከበረ ቁርኣን ነው። በተጠበቀ መጽሐፍ ውስጥ ነው። የተጥራሩት እንጂ ሌላ አይነካውም። ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው። በዚህ ንግግር እናንተ ቸልተኞች ናችሁን? ሲሳያችሁንም (ዝናብን) እናንተ የምታስተባበሉት ታደርጋላችሁን?*

* ድርሻችሁ ማስተባበል ታደርጋላችሁን ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ምክንያቱም ሪዝቅ የሚለውን ቃል ድርሻ ለማለት ስለሚቻል ነው።

فَلَوۡلَآ إِذَا بَلَغَتِ ٱلۡحُلۡقُومَ ٨٣ وَأَنتُمۡ حِينَئِذٖ تَنظُرُونَ ٨٤ وَنَحۡنُ أَقۡرَبُ إِلَيۡهِ مِنكُمۡ وَلَٰكِن
لَّا تُبۡصِرُونَ ٨٥ فَلَوۡلَآ إِن كُنتُمۡ غَيۡرَ مَدِينِينَ ٨٦ تَرۡجِعُونَهَآ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٨٧

83-87. ነፍስ ጉሮሮንንም በደረሰች ጊዜ። እናንተ ያን ጊዜ የምታዩ ስትሆኑ። እኛ ግን እናንተ አታዩም እንጂ ከናንተ ይልቅ ወደ እርሱ የቀረብን ስንሆን። የማትዳኙም ከሆናችሁ እውነተኞች እንደሆናችሁ (ነፍሲቱን ወደ አካሉ) ለምን አትመልሷትም?

فَأَمَّآ إِن كَانَ مِنَ ٱلۡمُقَرَّبِينَ ٨٨

88. እናም (ሟቹ) ከባለሟሎች ከሆነም፤

فَرَوۡحٞ وَرَيۡحَانٞ وَجَنَّتُ نَعِيمٖ ٨٩

89. ለእርሱ እረፍት መልካም ሲሳይና የመጠቀሚያ ገነት አለው።

وَأَمَّآ إِن كَانَ مِنۡ أَصۡحَٰبِ ٱلۡيَمِينِ ٩٠ فَسَلَٰمٞ لَّكَ مِنۡ أَصۡحَٰبِ ٱلۡيَمِينِ ٩١ وَأَمَّآ إِن كَانَ
مِنَ ٱلۡمُكَذِّبِينَ ٱلضَّآلِّينَ ٩٢ فَنُزُلٞ مِّنۡ حَمِيمٖ ٩٣ وَتَصۡلِيَةُ جَحِيمٍ ٩٤ إِنَّ هَٰذَا لَهُوَ حَقُّ
ٱلۡيَقِينِ ٩٥ فَسَبِّحۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلۡعَظِيمِ ٩٦

**90-96.** (ሟቹ) ከቀኝ ጓዶችም ከሆነ ከቀኝ ጓዶች ስለሆንክ ለአንተ ሰላም አላህ ይባላል። (ሟቹ) ከእነዚያ ከሚያስዋሹት ጠማማዎች ከሆነ ደግሞ ከፈላ ውሃ የሆነ መስተንግዶ አለለት። በገሀነም መቃጠልም አለለት። ይህ እርሱ እርግጠኛ እውነት ነው። የታላቁ ጌታህን ስም አጥራው።

**ከመከራይቱ ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-96) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡**

1. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
2. አላህን መፍራትና እምነት የሰው ልጅ ሊያሳድጉ ሽርክና ወንጀል ክብሩን ያሳጣል።
3. ወደ ዒባዳ ቅድሚያ ያላቸው ሰዎች ሁሉ በየትኛውም ቦታና ሰዓት ቅድሚያ እንዳላቸው፤
4. ግራኞች በዱንያም በአኼራም እድለቢሶች መሆናቸውን፤
5. የአኼራን ነገር በግልፅ ማረጋገጥ፤
6. ከጀነት በተለይም የቀደምት ሙስሊሞች እድል ማውሳት፤
7. በጀነት ያለው የከምር መጠጥ በዱንያ ካለው ኸምር ጋር ያለው ግንኙነት በስም እንጂ በምንም እንደማይገናኝ፤
8. ማንም ሰው የሚያገኘው ምንዳ እንደ ስራው መሆኑን።
9. አላህ ለሙዕሚኖች ሁሉ የዋለው ውለታ፤
10. በዱንያ ያረጁት ሰዎች ወጣት ሆነው እንደሚቀሰቀሱ፤
11. የጀነት ዋጋ እምነት ና አላህን በተገቢው መፍራት መሆኑን
12. የሙቶ መነሳት እውነት ማረጋገጥ፤
13. ስለ ሙቶ መነሳት ልዩ ልዩ ማስረጃዎችን መደርደር፤
14. አላህ በባሮች ላይ የዋለው ውለታ ማውሳት፤
15. አላህ ለዋለው ውለታ ማመስገንና፤
16. አላህን ማጥራት ግዴታ መሆኑን
17. አላህ በፈለገው እንዲምል፤
18. የአላህን ብቸኛ አምላክነትና የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ቁርኣን ከአላህ የወረደ ስለ መሆኑ፤
19. ቁርኣንን መጠበቅ በሙስሊሞች ላይ የተጣለ ግዴታ ስለመሆኑ፤
20. በአላህ ዲን ላይ አስቦ ዱንያን ለማግኘት መለማመጥ ክልክል መሆኑን፤
21. የሙቶ መነሳትን አውነትነት ማረጋገጥ፤
22. ሁሉም ሰው ከአላህ አቅም አንፃር ደካማ መሆኑን፤
23. የሰው ልጅ የተዘጋጀን ሰው ሩህ መመለስ ማንቃቱ ያለእሱ ምንም ማድረግ እንደማይችል፤
24. የቁርኣንን ህግጋት ሁሉ ፍትህና ምርጥ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የመከራይቱ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (57)
# የብረት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ሐዲድ)

سُورَةُ الحَدِيدِ

በመዲና የወረደ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (29) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

سَبَّحَ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ١

1. በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ አላህን አጠሩ። እርሱ ሁሉን አሸናፊ፤ ጥበበኛ ነው።

لَهُۥ مُلۡكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ يُحۡيِۦ وَيُمِيتُۖ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ٢

2. የሰማያትና የምድር ንግስና የእርሱ ብቻ ነው። ሕይወትን የሚሰጥና ሕይወትን የሚነሳ እሱው ነው። እርሱ ሁሉንም ነገር ቻይ ነውና።

هُوَ ٱلۡأَوَّلُ وَٱلۡأٓخِرُ وَٱلظَّٰهِرُ وَٱلۡبَاطِنُۖ وَهُوَ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٌ ٣

3. (እርሱ ከበፊቱ ምንም ያልቀደመ) የመጀመሪያ፤ (ፊት ያለ) (ከኋላው ምንም የሌለ የመጨረሻ) ብቻዉን ቀሪ፤ ከበላዩ ማንም የሌለ (ግልፅና የበላይ ስውርም ነው። እርሱ (በምድርም ሆነ በሰማይ ያለን) ሁሉ ነገር አዋቂ ነው።

هُوَ ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ فِي سِتَّةِ أَيَّامٖ ثُمَّ ٱسۡتَوَىٰ عَلَى ٱلۡعَرۡشِۖ يَعۡلَمُ مَا يَلِجُ فِي
ٱلۡأَرۡضِ وَمَا يَخۡرُجُ مِنۡهَا وَمَا يَنزِلُ مِنَ ٱلسَّمَآءِ وَمَا يَعۡرُجُ فِيهَاۖ وَهُوَ مَعَكُمۡ أَيۡنَ مَا كُنتُمۡۚ
وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ٤

4. እርሱ ያ! ሰማያትንና ምድርን በስድስት ቀናት ብቻ የፈጠረ ነው። ከዚያ በዐርሹ ላይ ከፍ* ያለ አምላክ ነው። ወደ ምድር የሚገባውንና ከእርሷ የሚወጣውን ያውቃል። ከሰማይ የሚወረደውንና ወደ እርሷ የሚወጣውን

ያውቃል። እርሱ የትም ብትሆኑ በእውቀቱ ከናንተው ጋር ነው። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

✷ በአል አዕራፍ (53) ኛው ላይ በሰፊው ተዘርዝሯል።

لَّهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ وَإِلَى ٱللَّهِ تُرْجَعُ ٱلْأُمُورُ ﴿٥﴾ يُولِجُ ٱلَّيْلَ فِى ٱلنَّهَارِ وَيُولِجُ ٱلنَّهَارَ فِى ٱلَّيْلِ ۚ وَهُوَ عَلِيمٌۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿٦﴾

5-6. የሰማያትና የምድር ንግስና የእርሱ ብቻ ነው። ነገሮች ሁሉ ወደ አላህ ይመለሳሉ። ሌሊትን በቀን ውስጥ ያስገባል። ቀንንም በሌሊት ውስጥ ያስገባል። እርሱም በልቦች ውስጥ የተደበቁትን ሁሉ አዋቂ ነው።

ءَامِنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَأَنفِقُوا۟ مِمَّا جَعَلَكُم مُّسْتَخْلَفِينَ فِيهِ ۖ فَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مِنكُمْ وَأَنفَقُوا۟ لَهُمْ أَجْرٌ كَبِيرٌ ﴿٧﴾

7. (ሰዎች ሆይ!) በአላህና በመልዕክተኛው እመኑ። አላህ በእርሱ ላይ ተተኪዎች ካደረጋችሁ ገንዘብ ዉስጥም ለግሱ✷። እነዚያ ከእናንተ ውስጥ በአላህ ያመኑትና የለገሱት ሁሉ ለእነርሱ ታላቅ ምንዳ አለላቸው።

✷ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ይህች ዓለም ዱንያ ጣፋጭና አረንጓዴ ናት። አላህ በዚህች ዓለም ውስጥ ወኪሉ አድርጓችኋል። ይህንን ተግባራችሁን ኃላፊነታችሁን እንዴት እንደምትወጡ ያመለከታል። ዱንያና ሴት ልጅ ተጠንቀቁ። የበኒ እስራኢል የመጀመሪያ ፈተና ሴት ልጅ ነበረች» ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ የመሰናባቻ ሐጅ ዕለት ተከታዩን ንግግር ሲያሰሙ አድምጫለሁ በማለት አስተላፈዋል፦ «አላህን ፍሩ፤ አምስት ወቅት ሶላቶችን ስገዱ፤ የረመዷንን ወር ፁሙ፤ ከገንዘባችሁ ዘካን ስጡ። መሪዎቻችሁን ታዘዙ፤ ጌታችሁ ያዘጋጀላችሁን ጀነት ትገባላችሁ»

وَمَا لَكُمْ لَا تُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ ۙ وَٱلرَّسُولُ يَدْعُوكُمْ لِتُؤْمِنُوا۟ بِرَبِّكُمْ وَقَدْ أَخَذَ مِيثَٰقَكُمْ إِن كُنتُم مُّؤْمِنِينَ ﴿٨﴾ هُوَ ٱلَّذِى يُنَزِّلُ عَلَىٰ عَبْدِهِۦٓ ءَايَٰتٍۭ بَيِّنَٰتٍ لِّيُخْرِجَكُم مِّنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِ ۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ بِكُمْ لَرَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴿٩﴾

8-9. (ሰዎች ሆይ!) ጌታችሁ ቃልኪዳናችሁን የያዘባችሁ ሲሆን መልዕክተኛው በጌታችሁ እንድታምኑ የሚጠራችሁ ሲሆን በአላህ የማታምኑበት ለእናንተ ምን ምክኒያት አላችሁ? እርሱ ያ ከጨለማዎች ወደ ብርሀን ሊያወጣችሁ ያ ግልፆች የሆኑን አንቀፆች በባሪያው ላይ የሚያወርድ ነው። አላህ ለእናንተ በእርግጥ ሩህሩህ፤ አዛኝ ነው።

وَمَا لَكُمْ أَلَّا تُنفِقُوا۟ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ وَلِلَّهِ مِيرَٰثُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ لَا يَسْتَوِى مِنكُم
مَّنْ أَنفَقَ مِن قَبْلِ ٱلْفَتْحِ وَقَٰتَلَ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ أَعْظَمُ دَرَجَةً مِّنَ ٱلَّذِينَ أَنفَقُوا۟ مِنۢ بَعْدُ وَقَٰتَلُوا۟ ۚ
وَكُلًّا وَعَدَ ٱللَّهُ ٱلْحُسْنَىٰ ۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ﴿١٠﴾

10. የሰማያትና የምድር ውርስ ለአላህ ብቻ ሲሆን በአላህ መንገድ የማትለግሱበት ምን ምክንያት አላችሁ? ከናንተ መካከል ከመካ መከፈት በፊት የለገሰና የተጋደለ ሰው ከተከፈተ በኋላ ከለገሰና ከተጋደለ ጋር አይስተካከልም። ከእነዚያ በኋላ ከለገሱትና ከተጋደሉት እነዚህ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸውና። ሁሉንም አላህ መልካሚቱን ተስፋ ቃል ገብቶላቸዋል። አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው።

ከብረት ምዕራፍ (10) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) አቡበክር አጠገባቸው በነበሩበት ወቅት መላዕኩ ጅብሪል መጥቶ አቡበክር ለምንድ ነው በደረቱ ላይ የተንጠለጠለች ኮት የለበሰው ሲላቸው ከፊት ለፊትህ ካፖርቱን ለእኔ ሲል አውጥቶ ስለነበረ ነው አሉት። ጅብሪልም መለስ አድርጎ በአላህ ሰላምታም አድርሰውና ጌታህ ይህን ድህነት ተቀበለህዋል ወይንስ ጠልተኸዋል በማለት ጠይቀው ነብዩ (ﷺ) ወደ አቡበክር ዞር ብለው ጅብሪል የአላህን ሰላም አድርሰህ ጌታህን እንዲህ ብሎሀል ሲሏቸው አቡበክር አልቅሰው በጌታዬ ላይ እቆጣለሁኝን? እኔ ከጌታዬ ጋር ተስማቻለሁ በማለታቸው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

مَّن ذَا ٱلَّذِى يُقْرِضُ ٱللَّهَ قَرْضًا حَسَنًا فَيُضَٰعِفَهُۥ لَهُۥ وَلَهُۥٓ أَجْرٌ كَرِيمٌ ﴿١١﴾

11. ያ! ለአላህ መልካም ብድርን የሚያበድርና ለእርሱ አላህ ምንዳውን የሚያነባብርለት ሰው ማን ነው? ለእርሱም መልካም ምንዳ አለው።

يَوْمَ تَرَى ٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتِ يَسْعَىٰ نُورُهُم بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَبِأَيْمَٰنِهِم بُشْرَىٰكُمُ ٱلْيَوْمَ
جَنَّٰتٌ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَا ۚ ذَٰلِكَ هُوَ ٱلْفَوْزُ ٱلْعَظِيمُ ﴿١٢﴾

12. ወንድ አማኞችንና ሴት አማኞችን በስተፊቶቻቸው በቀኞቻቸውም ብርሀናቸው የሚሮጥ ሲሆን በምታያቸው ቀን (ምንዳ አለላቸው)። ዛሬ ብስራታችሁ በውስጦቻቸው ዘወታሪዎች ስትሆን ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ናቸው ይባላሉ። ይህ እርሱ ታላቅ እድል ነው።

يَوْمَ يَقُولُ ٱلْمُنَٰفِقُونَ وَٱلْمُنَٰفِقَٰتُ لِلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱنظُرُونَا نَقْتَبِسْ مِن نُّورِكُمْ
قِيلَ ٱرْجِعُوا۟ وَرَآءَكُمْ فَٱلْتَمِسُوا۟ نُورًا فَضُرِبَ بَيْنَهُم بِسُورٍ لَّهُۥ بَابٌۢ بَاطِنُهُۥ فِيهِ ٱلرَّحْمَةُ
وَظَٰهِرُهُۥ مِن قِبَلِهِ ٱلْعَذَابُ ﴿١٣﴾

13. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የወንድ መናፍቃንና የሴት መናፍቃት ለእነዚያ በአላህ ለአመኑት ጠብቁን ከብርሀናችሁ እናበራለንና የሚሉበትን ቀን (አስታውስ)። ወደ ኋላችሁ ተመለሱ። ብርሀንንም እዚያው ፈልጉ ይባላሉ። በመካከላቸውም ለእርሱ ደጃፍ ባለው አጥር ይከለላል። ግቢው በውስጡ ገነት ያለበት ከውጪውም በኩሉ ደግሞ የእሳት (ስቃይ) ያለበት የሆነ (ደጃፍ ባለው አጥር)።

يُنَادُونَهُمْ أَلَمْ نَكُن مَّعَكُمْ ۖ قَالُوا۟ بَلَىٰ وَلَـٰكِنَّكُمْ فَتَنتُمْ أَنفُسَكُمْ وَتَرَبَّصْتُمْ وَٱرْتَبْتُمْ وَغَرَّتْكُمُ ٱلْأَمَانِىُّ حَتَّىٰ جَآءَ أَمْرُ ٱللَّهِ وَغَرَّكُم بِٱللَّهِ ٱلْغَرُورُ ﴿١٤﴾ فَٱلْيَوْمَ لَا يُؤْخَذُ مِنكُمْ فِدْيَةٌ وَلَا مِنَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ۚ مَأْوَىٰكُمُ ٱلنَّارُ ۖ هِىَ مَوْلَىٰكُمْ ۖ وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ﴿١٥﴾

14-15. ከናንተ ጋር አልነበርንምን? በማለት ይጠሩዋቸዋል። እውነት ነው እኛ ጋር ነበራችሁ። ግን እናንተ ነፍሶቻችሁን አጠፋችሁ በነብዩ አደጋዎችን ተጠባበቃችሁ ትጠራጠራላችሁም። የአላህ ትዕዛዝ እስከ መጣ ድረስ ከንቱ ምኞቶች አታለሏችሁ፤ አታላዩም ሰይጣን በአላህ መታገስ ሸነገላችሁ ይሏቸዋል። በመሆኑም ዛሬ ከናንተም ሆነ በአላህ ከካዱት ሰዎች ቤዛ አይወሰድም። መኖሪያችሁ የገሀነም እሳት ብቻ ናት። እርሷ ተገቢያችሁ ናትና። የገሀነም እሳት መመለሻነቷ ምን ትከፋም (ይሏቸዋል)።

۞ أَلَمْ يَأْنِ لِلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ أَن تَخْشَعَ قُلُوبُهُمْ لِذِكْرِ ٱللَّهِ وَمَا نَزَلَ مِنَ ٱلْحَقِّ وَلَا يَكُونُوا۟ كَٱلَّذِينَ أُوتُوا۟ ٱلْكِتَـٰبَ مِن قَبْلُ فَطَالَ عَلَيْهِمُ ٱلْأَمَدُ فَقَسَتْ قُلُوبُهُمْ ۖ وَكَثِيرٌ مِّنْهُمْ فَـٰسِقُونَ ﴿١٦﴾

16. ለእነዚያ በአላህ ለአመኑት ለአላህ ተግሳፅና ከቁርኣንም ለወረደው ልቦቻቸው ሊፈሩና እንደነዚያ በፊት መጽሐፍን እንደ ተሰጡትና በእነርሱ ላይ ጊዜ ስለ ረዘመባቸው ልቦቻቸው እንደ ደረቁ ህዝቦች የማይሆኑበት ጊዜ አልቀረበምን? ከእነርሱም ብዙዎቹ አመፀኞች ናቸው።

ٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ يُحْىِ ٱلْأَرْضَ بَعْدَ مَوْتِهَا ۚ قَدْ بَيَّنَّا لَكُمُ ٱلْـَٔايَـٰتِ لَعَلَّكُمْ تَعْقِلُونَ ﴿١٧﴾ إِنَّ ٱلْمُصَّدِّقِينَ وَٱلْمُصَّدِّقَـٰتِ وَأَقْرَضُوا۟ ٱللَّهَ قَرْضًا حَسَنًا يُضَـٰعَفُ لَهُمْ وَلَهُمْ أَجْرٌ كَرِيمٌ ﴿١٨﴾ وَٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦٓ أُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلصِّدِّيقُونَ ۖ وَٱلشُّهَدَآءُ عِندَ رَبِّهِمْ لَهُمْ أَجْرُهُمْ وَنُورُهُمْ ۖ وَٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ وَكَذَّبُوا۟ بِـَٔايَـٰتِنَآ أُو۟لَـٰٓئِكَ أَصْحَـٰبُ ٱلْجَحِيمِ ﴿١٩﴾

**17-19.** (ሰዎች ሆይ!) አላህ ምድርን ከሞተች በኋላ ህያው የሚደርጋት መሆኑን እወቁ፡፡ ይህን ታውቁ ዘንድ አንቀፆችን ለእናንተ በእርግጥ አብራራንላችሁ፡፡ የመፀወቱ ወንዶችና የመፀወቱ ሴቶች ለአላህ መልካምን ብድር ያበደሩ ሁሉ ለእነርሱም ምንዳ ይደራረብላቸዋል፡፡ ለእነርሱም መልካም የተከበረ ምንዳ አለላቸው፡፡ እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞቹ ያመኑ ሰዎች እነዚያ እነርሱ በጣም እውነቶኞች በጌታቸውም ዘንድ መስካሪዎች ናቸው፡፡ ለእነርሱም ምንዳቸው ብርሀናቸውም አለላቸው፡፡ እነዚያ በአላህ የካዱትና በአንቀፆቻችን ያስተባብሉ ሰዎች ደግሞ የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡

ٱعْلَمُوٓا۟ أَنَّمَا ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَا لَعِبٌ وَلَهْوٌ وَزِينَةٌ وَتَفَاخُرٌۢ بَيْنَكُمْ وَتَكَاثُرٌ فِى ٱلْأَمْوَٰلِ
وَٱلْأَوْلَـٰدِ ۖ كَمَثَلِ غَيْثٍ أَعْجَبَ ٱلْكُفَّارَ نَبَاتُهُۥ ثُمَّ يَهِيجُ فَتَرَىٰهُ مُصْفَرًّا ثُمَّ يَكُونُ حُطَـٰمًا ۖ
وَفِى ٱلْـَٔاخِرَةِ عَذَابٌ شَدِيدٌ وَمَغْفِرَةٌ مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضْوَٰنٌ ۚ وَمَا ٱلْحَيَوٰةُ ٱلدُّنْيَآ إِلَّا مَتَـٰعُ ٱلْغُرُورِ ﴿٢٠﴾

**20.** (ሰዎች ሆይ!) ቅርቢቱን ሕይወት ጨዋታና ዛዛታ ማጌጫም በመካከችሁም መፎካከሪያ በገንዘቦችና በልጆችም ብዛት መበላለጫ ብቻ መሆንዋን እወቁ፡፡ እርሷ በቃዩ ገበሬዎችን ቡቃያው እንደሚያስደስት ዝናብና ከዚያ በቃዩ እንደሚደርቅና ገርጥቶ እንደሚታየው ከዚያም የተሰባበረ እንደሚሆን ብጤ ነው፡፡ በመጨረሻይቱም ዓለም ለአጥፊዎች ብርቱ ቅጣት፤ ለትክክለኛ አማኞች ከአላህ ምህረትና ውዴታ አለ፡፡ የቅርቢቱ ሕይወት እኮ የመታለያ ጥቅም እንጂ ሌላ አይደለችም፡፡

سَابِقُوٓا۟ إِلَىٰ مَغْفِرَةٍ مِّن رَّبِّكُمْ وَجَنَّةٍ عَرْضُهَا كَعَرْضِ ٱلسَّمَآءِ وَٱلْأَرْضِ أُعِدَّتْ لِلَّذِينَ
ءَامَنُوا۟ بِٱللَّهِ وَرُسُلِهِۦ ۚ ذَٰلِكَ فَضْلُ ٱللَّهِ يُؤْتِيهِ مَن يَشَآءُ ۚ وَٱللَّهُ ذُو ٱلْفَضْلِ ٱلْعَظِيمِ ﴿٢١﴾

**21.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) በአላህና በመልዕክተኞች ላመኑት ወደ ተዘጋጀችውና የወርዷ ስፋት እንደ ሰማይና ምድር ወደ ሆነችም ገነት ተሽቀዳደሙ፡፡ ይህ የአላህ ችሮታ ነው፡፡ ለሚፈልገው ሰው ብቻ ይሰጠዋል፡፡ አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነውና፡፡

مَآ أَصَابَ مِن مُّصِيبَةٍ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَا فِىٓ أَنفُسِكُمْ إِلَّا فِى كِتَـٰبٍ مِّن قَبْلِ أَن نَّبْرَأَهَآ ۚ
إِنَّ ذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٌ ﴿٢٢﴾ لِّكَيْلَا تَأْسَوْا۟ عَلَىٰ مَا فَاتَكُمْ وَلَا تَفْرَحُوا۟ بِمَآ ءَاتَىٰكُمْ ۗ
وَٱللَّهُ لَا يُحِبُّ كُلَّ مُخْتَالٍ فَخُورٍ ﴿٢٣﴾ ٱلَّذِينَ يَبْخَلُونَ وَيَأْمُرُونَ ٱلنَّاسَ بِٱلْبُخْلِ ۗ
وَمَن يَتَوَلَّ فَإِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلْغَنِىُّ ٱلْحَمِيدُ ﴿٢٤﴾

**22-24.** በምድርም ሆነ በነፍሶቻችሁ መከራ ማንንም አታጋጥምም ሳንፈጥራት በፊት በመጽሐፍ የተመዘገበች ብትሆን እንጅ።✱ ይህ በአላህ ላይ ቀላሉ ነው። (ይህ ማሳወቃችን) ባመለጣችሁ ፀጋ ላይ እንዳታዝኑና አላህ በሰጣችሁ ነገር (በትዕቢት) እንዳትደሰቱ ነው። አላህ ኩራተኛንና ጉረኛን ሁሉ አይወድምና። (እነርሱም) እነዚያ የሚሰስቱና ሰዎችንም በስስት ላይ የሚያዙ ናቸው። ከእውነት የሚሸሽ ሰው ሁሉ ጉዳቱ ለራሱ ብቻ ነው። አላህም ተብቃቂ ምስጉን ነውና።

✱ ቲርሚዚይ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐብባስ እንዳስተላለፉት በአንድ ወቅት ከነብዩ (ﷺ) በኋላ ሳለሁ፦ «ልጅ ሆይ! እኔ የተወሰኑ ቃሎችን አስተምርሃለሁ።

1. የአላንህ ትዕዛዝ ጠብቅ እርሱም ይጠብቅሀል።
2. አላህን ጠብቀው ከፊት ለፊትህ ታገኘዋለህ።
3. ስትጠይቅ አላህን ጠይቅ፤
4. እርዳታን ከፈለክ በአላህ ተረዳ፤
5. ሕዝቦች ሁሉ ሊጠቅሙህ ቢሰባሰቡ አይጠቅሙህም። አላህ በእርግጥ የወሰነልህ ነገር ሲቀር። ሊጎዱህ ቢሰበሰቡ ሊጎዱህ አይችሉም። አላህ በእርግጥ ባንተ ላይ የወሰነብህ ነገር ቢሆን እንጂ። ብዕሮች ተነስተዋል ገፆችም ደርቃዋል።»

لَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا رُسُلَنَا بِٱلۡبَيِّنَٰتِ وَأَنزَلۡنَا مَعَهُمُ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡمِيزَانَ لِيَقُومَ ٱلنَّاسُ بِٱلۡقِسۡطِۖ وَأَنزَلۡنَا ٱلۡحَدِيدَ فِيهِ بَأۡسٞ شَدِيدٞ وَمَنَٰفِعُ لِلنَّاسِ وَلِيَعۡلَمَ ٱللَّهُ مَن يَنصُرُهُۥ وَرُسُلَهُۥ بِٱلۡغَيۡبِۚ إِنَّ ٱللَّهَ قَوِيٌّ عَزِيزٞ ﴿٢٥﴾

**25.** መልዕክተኞቻችንን በግልፅ ማስረጃዎች አጠናክረን በእርግጥ ላክን። ሰዎችም በትክክል ቀጥ እንዲሉ መጽሐፎችንና ሚዛንን ወደ እነርሱ አወረድን። ብረትንም ከውስጡ ብርቱ ኃይልና✱ ለሰዎችም መጠቃቀሚያዎች ያለበት ሲሆን አወረድን። አላህ ሃይማኖትንና መልዕክተኞችን በሩቁ ሆኖ የሚረዳውን ሰው ሊያውቅ (ሊገልፅ) አወረደው። አላህ ብርቱና አሸናፊ ነውና።

✱ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ስለ አላህ መልዕክት ሲነግሩን፦ «ከኛ መካከል በአላህ መንገድ ላይ የተጋደለ ወደ ጀነት ሄዷል» አሉ። ዑመርም ለነብዩ (ﷺ) «ግዳዩቻችን ጀነት ውስጥ ግዳዩቻቸው ደግሞ እሳት ውስጥ አይደሉምን?» አሏቸው። እሳቸውም «እንዴታ!» አሉ።

ለ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «ሰዎች ሆይ! በእርግጥ ጀነት በሰይፍ ጥላ ስር እንደሆነች እወቁ»

وَلَقَدۡ أَرۡسَلۡنَا نُوحٗا وَإِبۡرَٰهِيمَ وَجَعَلۡنَا فِي ذُرِّيَّتِهِمَا ٱلنُّبُوَّةَ وَٱلۡكِتَٰبَۖ فَمِنۡهُم مُّهۡتَدٖۖ وَكَثِيرٞ مِّنۡهُمۡ فَٰسِقُونَ ﴿٢٦﴾

26. ኑህንና ኢብራሂምን በእርግጥ ላክን። በዘሮቻቸውም ውስጥ ነብይነትንና መጽሐፍን አደረግን። ከእነርሱም መካከል ቅን ሰው አለ። ከእነርሱም መካከል ብዙዎቹ አመፀኞች ናቸው።

ثُمَّ قَفَّيْنَا عَلَىٰٓ ءَاثَٰرِهِم بِرُسُلِنَا وَقَفَّيْنَا بِعِيسَى ٱبْنِ مَرْيَمَ وَءَاتَيْنَٰهُ ٱلْإِنجِيلَ ۖ وَجَعَلْنَا فِى قُلُوبِ
ٱلَّذِينَ ٱتَّبَعُوهُ رَأْفَةً وَرَحْمَةً ۚ وَرَهْبَانِيَّةً ٱبْتَدَعُوهَا مَا كَتَبْنَٰهَا عَلَيْهِمْ إِلَّا ٱبْتِغَآءَ رِضْوَٰنِ ٱللَّهِ
فَمَا رَعَوْهَا حَقَّ رِعَايَتِهَا ۖ فَـَٔاتَيْنَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مِنْهُمْ أَجْرَهُمْ ۖ وَكَثِيرٌ مِّنْهُمْ فَٰسِقُونَ ﴿٢٧﴾

27. ከዚያ በእነርሱ ፈለጋቸው ላይ መልዕክተኞችን አከታተልን። የመርየም ልጅን ዒሳንም አስከተልን። ኢንጂልንም ሰጠነው። በእነዚያም በተከተሉት ሰዎች ልቦች ውስጥ መለዘብንና እዝነትን አዲስ የፈጠሩዋትንም ምንኩስና አደረግን። በእነርሱ ላይ ምንኩስናን አልደነገግንም። ግን የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ሲሉ ከራሳቸው ፈጠሩዋት። ተገቢ አጠባበቅም አልጠበቋትም። ከእነርሱም መካከል በአላህ ላመኑት ምንዳቸውን ሰጠናቸው። ከእነርሱ ብዙዎቹ ግን አመፀኞች ናቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ وَءَامِنُوا۟ بِرَسُولِهِۦ يُؤْتِكُمْ كِفْلَيْنِ مِن رَّحْمَتِهِۦ وَيَجْعَل
لَّكُمْ نُورًا تَمْشُونَ بِهِۦ وَيَغْفِرْ لَكُمْ ۚ وَٱللَّهُ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ﴿٢٨﴾

28. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! አላህን ፍሩ። በመልክተኛውም እመኑ። ከችሮታው ሁለትን ክፍሎች ይሰጣችኋልና። ለእናተም የምትሄዱበትን ብርሃን ያደርግላችኋል። ለእናንተም ወንጀላችሁን ይምራል። አላህ መሀሪና አዛኝ ነው።*

* ለ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ (ﷺ) ብለዋል፡- «የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ! ከ አይሁድ እና ክርስቲያኖች መካከል ስለእኔ ሰምቶ እኔ በተላኩበት መልዕክት ሳያምን የሚሞት ማንም የለም ከእሳት ሰዎች በስተቀር።»

لِّئَلَّا يَعْلَمَ أَهْلُ ٱلْكِتَٰبِ أَلَّا يَقْدِرُونَ عَلَىٰ شَىْءٍ مِّن فَضْلِ ٱللَّهِ ۙ وَأَنَّ ٱلْفَضْلَ بِيَدِ ٱللَّهِ
يُؤْتِيهِ مَن يَشَآءُ ۚ وَٱللَّهُ ذُو ٱلْفَضْلِ ٱلْعَظِيمِ ﴿٢٩﴾

29. ይህ የመጽሐፍ ሰዎች ከአላህ ችሮታ በምንም ላይ የማይችሉ መሆናቸውንና ችሮታውም አላህ ለሚሻው ሰው ብቻ የሚሰጠው በእሱ እጅ ብቻ መሆኑን እንዲያውቁ ነው። አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው።

**ከብረት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-29) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በአላህና በመልዕክተኛው (ﷺ) ማመን፤
2. በአላህ ዲን ላይ ንብረትንም ሆነ ጉልበትን ማፍሰስ ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ፤
3. አላህ ለባሮቹ ምን ያህል አዛኝና ሩህሩህ እንደሆነ፤
4. በችግር ጊዜ መስጠት አጅሩ የበለጠ መሆኑን፤
5. በአጠቃላይ መስጠት በኢስላም ከፍተኛ ምንዳ ያለውና አንድ በሺ የሚመነዳበት አጋጣሚ እንዳለ መግለፅ፤
6. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
7. እድለኝነት ማለት የዱንያ ሀብቶችን ማካተትና የዓለም ደስታና ፌስታ ማግኘት ሳይሆን ከገሀነም እሳት ሁኖ ጀነት መግባት እንደሆነ፤
8. ምእመናን ወደ ጀነት ከመግባታቸው በፊት ከሚለገስላቸው ብስራት አንድ መላኢኮች ተቀብለዋቸው መዝገባቸውን በቀኝ እጃቸው መስጠትና በፊት ለፊታቸውና በቀኛቸው ብርሃን መኖሩ መሆኑን፤
9. ከአስመሳዮች ባህሪያት መካከል አንዳንዶችን መግለፅ እነሱም ክህደትን በውስጣቸው መደበቅ ሙስሊሞችን ለማጥቃትም አጋጣሚ መጠባበቅና ሁል ጊዜም ተጠርጣሪዎች መሆናቸውን፤
10. አላህን ከማስታወስ እንዳንዘነጋ ማስታወስ፤
11. ሙስሊሞችን መምከርና ማስተማር አስፈላጊነቱ፤
12. ምድር በዝናብ ሕይወት እንደምትዘራ ሁሉ የሰዎች መንፈስም በዕውቀትና ምክር ህይወት እንደሚዘራ ማስተማር፤
13. ለአላህ አበዳሪዎች በትክክል በአላህና በመልዕክተኛው አማኞች እውነተኞችና ሰማዕታት በማለት መከፋፈሉ፤
14. በዱንያ እንዳንታለል ማስጠንቀቅ፤
15. የአላህን ምህረት ለማግኘት መሽቀዳደም፤
16. ብረት ብዙ ጥቅሞች እንዳሉት በተለይ በአሁኑ ዘመን በደንብ ተደርሶበታል። ከአንድ ሺህ አራት መቶ ዓመት በፊት የተደረሰበት ጥቅም በጣም ትንሽ ነበር። ሰይፎች ጦሮች ጦር ልብሶችና አንዳንድ የቤት እቃዎች ይሰራበት ይሆናል እንጂ ብዙ ነገር አሁን ግን የብረትን ጥቅም በቁጥር የማይዘለቅ የጦር መሳሪያዎች በየዓይነታቸው ከእጅ ቦንብ እስከ ግዙፍ የባህር መርከቦች የሚሠሩት ከብረት ነው። እኒያ በዓለም ላይ የተሰሩ ታላላቅ ግድቦ በብረትና በሲሚንቶ ነው የሚሰሩት። የእኒያ ግዙፍ ፋብሪካዎች ሞተሮችና ማሺኖችና ቋቶች ከዚሁ ከብረት ነው የተሰሩት። ሱብሃነላህ!
17. የቀደር ጉዳይ ማሳመን፤
18. የቀደርን ጉዳይ የመማር ምክንያቶች፤
19. ኩራትና ትዕቢት፤
20. አላህ ለህዝቦቹ የዋለውን ውለታ ማሳወቅ፤
21. አላህ ለባሮቹ ነብያትን በመላክ የዋለው ውለታ፤
22. አላህ ለህዝቦቹ ነብያት ሲላክ ሁሉም አሚን ብሎ እንደማይቀበል፤
23. ዒሳንና ባልደረቦቹን ማሞገስ፤
24. በዲን ቢድዓ የተባለ ሁሉ ክልክል ስለ መሆኑ፤
25. የመፅሐፍ ባለቤቶች ቢጠቀሙበት ኑሮ፤
26. የእምነትና የአላህን ፍራቻ ትልቅነት፤
27. የመፅሐፍት ሰዎች ጀነት የእኛ ብቻ ናት የሚሉትን አባባል ሀሰትነት ማጋለጥ እንማራለን።

**በአላህ ፈቃድ የብረት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።**

# ምዕራፍ (58)
# የተከራካሪዋ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ሙጃዲለህ)

سُورَةُ المُجَادلَة

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ (22) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

قَدۡ سَمِعَ ٱللَّهُ قَوۡلَ ٱلَّتِي تُجَٰدِلُكَ فِي زَوۡجِهَا وَتَشۡتَكِيٓ إِلَى ٱللَّهِ
وَٱللَّهُ يَسۡمَعُ تَحَاوُرَكُمَآۚ إِنَّ ٱللَّهَ سَمِيعُۢ بَصِيرٌ ١

1. *(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ የዚያችን በባሏ ጉዳይ ላይ የምትከራከርህንና ወደ አላህ ስሞታን የሙታሰሙተውን (ሴት) ቃል ሰማ። አላህ በንግግር መመላለሳችሁን (መወያየታችሁን) ይሰማል። አላህ (ለሚባለው) ሁሉ ሰሚ (ለሚፈፅመው ሁሉ ነገር) አዋቂ ነውና።

✷ ክፍል ሃያ ስምንተኛ

የተከራካሪዋ ሴት ምዕራፍ ከ (1-4) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ኸውለህ ቢንቱ ሰዕለባ የተባለች አንዲት ሴት ሰሀቢይ በቀላል ነገር አውስ ቢን ሳቢት ከተባለ ሱሃቢ ባሏ ጋር ተኮራርፈው ሳሉ «ከዛሬ ጀምሮ አንቺ እንደ እርም ይህ ቃል ሚስቱን ላለመገናኘት የተጠቀመው ቃል ነው ነሽ» ስላላት ወደ ነብዩ በመምጣት ይህ ሰው ወጣትነቴን በልቶ እድሜየ ሲገፋና መውለድ ሳቋርጥ እንደ እናቴ ነሽ አለኝ። ምን ይሻለኛል? አለቻቸው። ነብዩ (ﷺ) (መልሱን ከአላህ ዘንድ ወህይ በመጠበቅ) ምንም መፍትሄ እስካሁን እኔ ጋር የለሽም በማለታቸው እሳቸው አጠገብ ቁማ ጌታየ ሆይ! ወደ አንተ ስሞታየን አቀርባለሁ እያለች ስታማርር ነው እነኚህ አናቅፅ የወረዱት። አንዲት ባሪያን ነፃ ይበል ንገሪው ሲሏት ምንም የለውም እኮ በማለት ስትመልስ እሺ ሁለት ወራትን በተከታታይ ይፁም በሚሏፅ ግዜም ሽማግሌ እኮ ነው አንቱ የአላህ መልክተኛ አይችልም አለቻቸው.... ስለዚህ ታሪክ ተፀምርነት እሜቱ እሜቴ ሲናገሩ ኸውላ ነብዩን (ﷺ) ስለዚህ ጉዳይ ስታናግር ግማሽ አባባሏን ብቻ እሰማ ነበር እንጂ ሙሉ በሙሉ አልሰማሁም። ሁሉን ነገር የሰማው ጌታ አላህ ግን አንድም ነገር ሳይቀር ስምቷት ቁርኣን አወረደላት በማለት ገልፀውታል። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ٱلَّذِينَ يُظَٰهِرُونَ مِنكُم مِّن نِّسَآئِهِم مَّا هُنَّ أُمَّهَٰتِهِمۡۖ إِنۡ أُمَّهَٰتُهُمۡ إِلَّا ٱلَّٰٓـِٔي وَلَدۡنَهُمۡۚ
وَإِنَّهُمۡ لَيَقُولُونَ مُنكَرٗا مِّنَ ٱلۡقَوۡلِ وَزُورٗاۚ وَإِنَّ ٱللَّهَ لَعَفُوٌّ غَفُورٞ ٢

**2.** እነዚያ ከናንተ ውስጥ ሚስቶቻቸውን እንደእናቶቻቸው ጀርባዎች ይሁኑብን በማለት የሚምሉ ሰዎች እነርሱ እናቶቻቸው አይደሉም። ትክክለኛ እናቶቻቸው እነዚያ የወለዷቸው ሴቶች ብቻ ናቸው። እነርሱ በዚህ ቃል የተጠላ ንግግርንና ውሸትን በእርግጥ ይናገራሉ። አላህ ለሚፀፀት ሰው ሁሉ ይቅር ባይና መሀሪ ነው።

وَٱلَّذِينَ يُظَٰهِرُونَ مِن نِّسَآئِهِمۡ ثُمَّ يَعُودُونَ لِمَا قَالُواْ فَتَحۡرِيرُ رَقَبَةٖ مِّن قَبۡلِ أَن يَتَمَآسَّاۚ
ذَٰلِكُمۡ تُوعَظُونَ بِهِۦۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ٣ فَمَن لَّمۡ يَجِدۡ فَصِيَامُ شَهۡرَيۡنِ مُتَتَابِعَيۡنِ
مِن قَبۡلِ أَن يَتَمَآسَّاۖ فَمَن لَّمۡ يَسۡتَطِعۡ فَإِطۡعَامُ سِتِّينَ مِسۡكِينٗاۚ ذَٰلِكَ لِتُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦۚ
وَتِلۡكَ حُدُودُ ٱللَّهِۗ وَلِلۡكَٰفِرِينَ عَذَابٌ أَلِيمٌ ٤

**3-4.** እነዚያ ሚስቶቻቸውን እንደእናቶቻቸው ጀርባዎች ይሁኑብን በማለት የሚምሉና ከዚያ ወደ ተናገሩት የሚመለሱ ሳይነካኩ በፊት በባርነት የተያዘችዋን ጫንቃ[*1] ነፃ ማውጣት ግዴታ አለባቸው። ይህ ህግ (የተጠቀሰው ህግ) በእርሱ ትገሰፁበታላችሁ።[*2] አላህ ለምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው። ይህን ላላገኘም[*3] ሰው ከመነካካታቸው በፊት ሁለት ተከታታይ[*4] ወሮችን መፆም አለበት። ይህን ላልቻለም ሰው ስልሳ ድሆችን ማብላት አለበት። ይህ በመልዕክተኛው እንድታምኑ ነው። እነኚህ ህግጋት የአላህ ህግጋት ናቸው። እናም አትተላለፏቸው። ለከሓዲያንም ሁሉ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው።

*1 ወንድ ባሪያን ወይም ሴት ባሪያን ከባርነት ኑሮ ነፃ ማውጣት አለባቸው ማለት ነው።

*2 ሚስትን በማናለብኝነት «አንቺ እንደ እናቴ ነሽ» ከማለት ትመከሩበታላችሁ።

*3 በእጁ የሌለውና መግዛትም አቅም የሌለው ወይም የሚገዛ ባሪያ ፈልጎ በገበያ ላይ ያጣ።

*4 አንድም ቀን ሲያፈጥር ቢሆን እናም ያለበቂ ምክኒያት ካፈጠረ በአዲስ ይጀምር። በቀንም ሆነ በማታ ሆን ብሎ ከእርሷ ጋር ግንኙነት ቢፈፅምም እንደዚሁ እንደ አዲስ ይጀምር።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحَآدُّونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ كُبِتُواْ كَمَا كُبِتَ ٱلَّذِينَ مِن قَبۡلِهِمۡۚ وَقَدۡ أَنزَلۡنَآ ءَايَٰتِۭ
بَيِّنَٰتٖۚ وَلِلۡكَٰفِرِينَ عَذَابٞ مُّهِينٞ ٥ يَوۡمَ يَبۡعَثُهُمُ ٱللَّهُ جَمِيعٗا فَيُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوٓاْۚ أَحۡصَىٰهُ
ٱللَّهُ وَنَسُوهُۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ شَهِيدٌ ٦

**5-6.** ግልፅ ማስረጃዎችን ያወረድን ስንሆን እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩ ሰዎች እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩ ሰዎች እንደተዋረዱት ሁሉ ተዋርደዋል። ለከሓዲያን አዋራጅ ቅጣት አለባቸው። አላህ ሁላቸውንም በአንድ አድርጎ (አንድም ሳይቀር በአንድ ዓይነት) በሚቀሰቅሳቸው ቀን

(ይቀጣቸዋል)፡፡ ከዚያ በዚህ ዓለም የሰሩትን መጥፎ ነገር ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ እነርሱ የረሱት ሲሆን መዝገባቸው ተመዝግቦ ያገኙታል፡፡ አላህ ግን አንድም ሳይቀር አውቆታል፡፡ አላህ ሁሉንም ነገር ተመልካች ነውና፡፡

أَلَمْ تَرَ أَنَّ ٱللَّهَ يَعْلَمُ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِى ٱلْأَرْضِ ۖ مَا يَكُونُ مِن نَّجْوَىٰ ثَلَٰثَةٍ إِلَّا هُوَ
رَابِعُهُمْ وَلَا خَمْسَةٍ إِلَّا هُوَ سَادِسُهُمْ وَلَآ أَدْنَىٰ مِن ذَٰلِكَ وَلَآ أَكْثَرَ إِلَّا هُوَ مَعَهُمْ أَيْنَ مَا
كَانُوا۟ ۖ ثُمَّ يُنَبِّئُهُم بِمَا عَمِلُوا۟ يَوْمَ ٱلْقِيَٰمَةِ ۚ إِنَّ ٱللَّهَ بِكُلِّ شَىْءٍ عَلِيمٌ ٧

7. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አላህ በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን አታውቅምን? በእውነቱ ሁሉንም አካቧል፡፡ የሶስት ሰዎች መንሾካሾክ አይከሰትም፤ አላህ አራተኛው ቢሆን እንጂ፤ የአምስትም ሰዎች መንሾካሾክ አይከሰትም እርሱ ስድስተኛ ቢሆን እንጂ፤ ከዚያ ያነሰም ይሁን የበዛ ሰው መሾካሾክ አይከሰትም እርሱ ባሉበት ቦታ አብሮአቸው ቢሆን እንጂ፡፡ ከዚያ በትንሳኤ ቀን የሰሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል፡፡ አላህ ሁሉን ነገር አዋቂ ነው፡፡

أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ نُهُوا۟ عَنِ ٱلنَّجْوَىٰ ثُمَّ يَعُودُونَ لِمَا نُهُوا۟ عَنْهُ وَيَتَنَٰجَوْنَ بِٱلْإِثْمِ وَٱلْعُدْوَٰنِ
وَمَعْصِيَتِ ٱلرَّسُولِ ۖ وَإِذَا جَآءُوكَ حَيَّوْكَ بِمَا لَمْ يُحَيِّكَ بِهِ ٱللَّهُ وَيَقُولُونَ فِىٓ أَنفُسِهِمْ لَوْلَا
يُعَذِّبُنَا ٱللَّهُ بِمَا نَقُولُ ۚ حَسْبُهُمْ جَهَنَّمُ يَصْلَوْنَهَا ۖ فَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ٨

8. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ወደ እነዚያ በመጥፎ ነገር ከመመሳጠር ወደ ተከለከሉት፤ ከዚያ ከእርሱ ወደ ተከለከሉት ነገር ወደ ሚመልሱትና በኃጢአትና ድንበር በማለፍ መልዕክተኛውን በመቃወም ወደ ሚመሳጠሩ አላየህምን? (ሰላም ሊሉ) ወደ አንተ በመጡ ጊዜ አላህ ባላናገረህ ቃል ያናግሩሃል፡፡ በነፍሶቻቸው (በውስጣቸው) (ይህ ሰው) (ነብይ ከሆነ) በምንለው ነገር አላህ አይቀጣንም ኖሮአልን? ይላሉ፡፡ ገሀነም የሚገቡባት ሲሆኑ (ከአሁኑ ሞት ይልቅ) በቂያቸው ናት፡፡ ገሀነምም መመለሻነቷ ከፋች!

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓا۟ إِذَا تَنَٰجَيْتُمْ فَلَا تَتَنَٰجَوْا۟ بِٱلْإِثْمِ وَٱلْعُدْوَٰنِ وَمَعْصِيَتِ ٱلرَّسُولِ وَتَنَٰجَوْا۟
بِٱلْبِرِّ وَٱلتَّقْوَىٰ ۖ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ٱلَّذِىٓ إِلَيْهِ تُحْشَرُونَ ٩ إِنَّمَا ٱلنَّجْوَىٰ مِنَ ٱلشَّيْطَٰنِ لِيَحْزُنَ
ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ وَلَيْسَ بِضَآرِّهِمْ شَيْـًٔا إِلَّا بِإِذْنِ ٱللَّهِ ۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلْيَتَوَكَّلِ ٱلْمُؤْمِنُونَ ١٠

**9-10.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በተመሳጠራችሁ ጊዜ በኃጢአት ወሰንን በማለፍና መልዕክተኛውንም በመቃወም አትሾካሾኩ ግን በበጎ ስራና አላህን በመፍራት ተወያዩ። ያንንም ወደ እርሱ የምትሰበሰቡበትን አላህን ፍሩ። በመጥፎ መመሳጠር ከሰይጣን ማስዋብና ማሳመር የሚመጣ ብቻ ነው። እነዚያ ያመኑ ሙስሊሞች ያዝኑ ዘንድ (ሰይጣን ይቀሰቅሰዋል)። በአላህ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ሰይጣንም መመሳጠር በምንም ነገር አይጎዳቸውም። እናም አማኞች በአላህ ብቻ ይመኩ።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا قِيلَ لَكُمْ تَفَسَّحُواْ فِى ٱلْمَجَـٰلِسِ فَٱفْسَحُواْ يَفْسَحِ ٱللَّهُ لَكُمْ ۖ
وَإِذَا قِيلَ ٱنشُزُواْ فَٱنشُزُواْ يَرْفَعِ ٱللَّهُ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ مِنكُمْ وَٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلْعِلْمَ دَرَجَـٰتٍ ۚ
وَٱللَّهُ بِمَا تَعْمَلُونَ خَبِيرٌ ١١

**11.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ለእናንተ በመቀመጫዎች ስፍራ ተስፋፉ በተባላችሁ ጊዜ ስፍራን አስፉ። አላህ በጀነት ያሰፋላችኋልና። ተነሱ በተባለም ጊዜ ተነሱ። አላህ ከናንተ መካከል እነዚያን በትክክል ያመኑትንና እነዚያንም እውቀትን የተሰጡትን በደረጃዎች በዚች ዓለምም ሆነ በአኼራ ከፍ ያደርጋል። አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጥ አወቂ ነውና።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا نَـٰجَيْتُمُ ٱلرَّسُولَ فَقَدِّمُواْ بَيْنَ يَدَىْ نَجْوَىٰكُمْ صَدَقَةً ۚ
ذَٰلِكَ خَيْرٌ لَّكُمْ وَأَطْهَرُ ۚ فَإِن لَّمْ تَجِدُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌ ١٢

**12.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ከመልዕክተኛው ጋር በተወያያችሁ ጊዜ ከመወያየታችሁ በፊት ምፅዋትን አስቀድሙ። (ሰደቃ ስጡ)። ይህ (ምፀዋትን አስቀድሞ መስጠት) ለእናንተ መልካምና አጥሪ ነው። ባታገኙም ምንንም (ሳትከፈሉ) ሳትሰጡ (ብትወያዩ ችግር የለባችሁም)። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

ءَأَشْفَقْتُمْ أَن تُقَدِّمُواْ بَيْنَ يَدَىْ نَجْوَىٰكُمْ صَدَقَـٰتٍ ۚ فَإِذْ لَمْ تَفْعَلُواْ وَتَابَ ٱللَّهُ عَلَيْكُمْ
فَأَقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُواْ ٱلزَّكَوٰةَ وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ ۚ وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ١٣

**13.** ከውይይታችሁ በፊት ምፅዋቶችን በማስቀደም ድህነትን ፈራችሁን? የታዘዛችሁትን ባልሰራችሁ ጊዜ አላህ ከናንተ ፀፀትን የተቀበለ ሲሆን ሶላትን ስገዱ፤ ዘካንም ስጡ፤ አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ። አላህ ውስጠ አዋቂ ነውና።

۞ أَلَمۡ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ تَوَلَّوۡاْ قَوۡمًا غَضِبَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِم مَّا هُم مِّنكُمۡ وَلَا مِنۡهُمۡ وَيَحۡلِفُونَ عَلَى
ٱلۡكَذِبِ وَهُمۡ يَعۡلَمُونَ ١٤ أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدًاۖ إِنَّهُمۡ سَآءَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ١٥
ٱتَّخَذُوٓاْ أَيۡمَٰنَهُمۡ جُنَّةٗ فَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِ فَلَهُمۡ عَذَابٞ مُّهِينٞ ١٦ لَّن تُغۡنِيَ عَنۡهُمۡ
أَمۡوَٰلُهُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُهُم مِّنَ ٱللَّهِ شَيۡـًٔاۚ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِۖ هُمۡ فِيهَا خَٰلِدُونَ ١٧ يَوۡمَ
يَبۡعَثُهُمُ ٱللَّهُ جَمِيعٗا فَيَحۡلِفُونَ لَهُۥ كَمَا يَحۡلِفُونَ لَكُمۡ وَيَحۡسَبُونَ أَنَّهُمۡ عَلَىٰ شَيۡءٍۚ أَلَآ إِنَّهُمۡ
هُمُ ٱلۡكَٰذِبُونَ ١٨ ٱسۡتَحۡوَذَ عَلَيۡهِمُ ٱلشَّيۡطَٰنُ فَأَنسَىٰهُمۡ ذِكۡرَ ٱللَّهِۚ أُوْلَٰٓئِكَ حِزۡبُ ٱلشَّيۡطَٰنِۚ
أَلَآ إِنَّ حِزۡبَ ٱلشَّيۡطَٰنِ هُمُ ٱلۡخَٰسِرُونَ ١٩

**14-19.** ወደ እነዚያ አላህ በእነርሱ ላይ የተቆጣባቸውን ህዝቦች (አይሁዶች) ወደ ተወዳጁት (መናፍቃን) አላየህምን? እነርሱ ከናንተ አይደሉም ከእነርሱም አይደሉም እነርሱም። እያወቁ በውሸት ይምላሉ። አላህ ለእነርሱ ብርቱ ቅጣትን አዘጋጀ። እነርሱ ይሰሩት የነበሩት መጥፎ ስራ ምንኛ ከፋ! መሓሎቻቸውን ጋሻ አድርገው ያዙ። ሰዎችንም ከአላህ መንገድ አገዱ። ስለዚህ ለእነርሱ አዋራጅ ቅጣት አለባቸው። ገንዘቦቻቸውንና ልጆቻቸውን ከአላህ ቅጣት ምንም ከእነርሱ አያድኗቸውም። እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው። እነርሱ በእርሷ ውስጥ ዘወታሪዎች ናቸው። (ይህ የሚሆነው) አላህ የተሰበሰቡ ሆነው በሚያስነሳቸው ቂያማ ቀን ነው። ለእናንተ እንደ ሚምሉላችሁ፤ እነርሱ በሚጠቅም ነገር ላይ መሆናቸውን የሚያስቡ ሆነው ለእርሱም ለአላህ ይምላሉ። ሙስሊሞች አስተዉሉ። ውሸታሞች እነርሱ ብቻ ናቸው። በእነርሱም ላይ ሰይጣን ተሾመባቸው (ተመቻቸባቸው)። እናም አላህን ማስታወስን አስረሳናቸው ትዕዛዛቱን ተው። እነዚያ የሰይጣን ጭፍሮች ቡድኖች ሰራዊቶች ናቸው። ሙስሊሞች አስተዉሉ። የሰይጣን ጭፍሮች ቡድኖች ከሳሪዎች እነርሱ ናቸው።

ከተከራካሪዋ ሴት ምዕራፍ ከ (14-19) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት:- ኢብኑ አቢሐቲም፤ ጦቦራኒ እና ሐኪም በዘገቡት ታሪክ «የአቡዐበይዳህ አባት በበድር እለት ሆን ብሎ ልጁን አቡዑበይዳህን ለመግደል ያድን ነበር። አቡዑበይዳህ ግን ከፊት ለፊቱ እየሸሹ ከአባታቸው ጋር ፊት ለፊት ላለመገናኘትና በእጃቸው እንዳይሞት ቢሞክሩም አባታቸው በግድ ስለመጣበቸው ገደሉት።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يُحَآدُّونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓ أُوْلَٰٓئِكَ فِي ٱلۡأَذَلِّينَ ٢٠ كَتَبَ ٱللَّهُ لَأَغۡلِبَنَّ أَنَا۠ وَرُسُلِيٓۚ
إِنَّ ٱللَّهَ قَوِيٌّ عَزِيزٞ ٢١

**20-21.** እነዚያ አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩ ሁሉ እነዚያ በዱንያም ሆነ በአኺራ በጣም ከተዋረዱ ወገኖች ውስጥ ናቸው። አላህ እኔ አሸንፋለሁ መልዕክተኞቼም እንዲሁ ያሸንፋሉ ሲል ድሮውኑ ጽፏል። አላህ ብርቱና አሸናፊ ነውና።

لَّا تَجِدُ قَوْمًا يُؤْمِنُونَ بِٱللَّهِ وَٱلْيَوْمِ ٱلْءَاخِرِ يُوَآدُّونَ مَنْ حَآدَّ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ وَلَوْ كَانُوٓاْ
ءَابَآءَهُمْ أَوْ أَبْنَآءَهُمْ أَوْ إِخْوَٰنَهُمْ أَوْ عَشِيرَتَهُمْ ۚ أُوْلَٰٓئِكَ كَتَبَ فِى قُلُوبِهِمُ ٱلْإِيمَٰنَ وَأَيَّدَهُم
بِرُوحٍ مِّنْهُ ۖ وَيُدْخِلُهُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَا ۚ رَضِىَ ٱللَّهُ عَنْهُمْ
وَرَضُواْ عَنْهُ ۚ أُوْلَٰٓئِكَ حِزْبُ ٱللَّهِ ۚ أَلَآ إِنَّ حِزْبَ ٱللَّهِ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٢٢﴾

**22.** በአላህና በመጨረሻው ቀን የሚያምኑትን ህዝቦች አላህንና መልዕክተኛውን የሚከራከሩት ሰዎች አባቶቻቸውን ወይም ልጆቻቸውን ወይም ወንድሞቻቸውን ወይም ዘመዶቻቸው ቢሆኑም እንኳ የሚወዳጁ ሆነው አታገኛቸውም። እነዚያ አላህ በልቦቻቸው ውስጥ እምነትን ጽፏል። ከእነርሱም በሆነ መንፈስ ደግፏቸዋል። ከስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች በውስጣቸው ዘወታሪዎች ሲሆኑ ያስገባቸዋል። አላህ ተግባራቸውን ወዷል። እነርሱም የእርሱን ችሮታ ወደዋል። እነዚያ የአላህ ህዝቦች ናቸው። ንቁ! የአላህ ህዝቦች ምኞታቸውን የሚያገኙ እነርሱ ናቸው።

### ከተከራካሪዋ ሴት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-22) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ

1. አላህ የባሮቹን ችግር በመስማትም ሆነ በሁሉ ነገር የተሟላ አቅምና ርህራሄ ያለው መሆኑን፤
2. ሚስትን እንደ እናቴ ናሽ ማለት አላህ የሚጠላው ክልክል ነገር መሆኑን፤
3. ሚስትን እንደ እናቴ ነሽ ያለና ወደ እሷም ለመመለስ የፈለገ ሰው ቅጣቱ ምን እንደሆነ፤
4. ባሪያን ነፃ በማውጣቱ ረገድ ወንድ፤ ሴት፤ ህፃን ወይም አዋቂንም ቢሆን ነፃ የሚያወጣው ልዩነት የለውም፤
5. ቅጣትን በፆም ለመወጣት የፈለገ ሰው በፆም ሊያሳልፋቸው የሚገባውን ሁለት ወራት ያለማቋረጥ አንድም ቀን እንኳን መፆም ይኖርበታል። ያቋረጠ ከሆነ ግን እንደ አዲስ አንድ ብሎ መጀመር እንዳለበት፤
6. እናት ማለት የወለደች እናት ብቻ መሆኗን፤
7. በአላህ ላይ መመካት፤ አላህን እና መልዕክተኛውን ነብዩ (ﷺ) መታዘዝ የእምነት አንኳር መሆኑን፤
8. መወያየትና ምክክር ማድረግ ለኸይር ነገር ብቻ ካልሆነ በስተቀር የተከለከለ መሆኑን፤
9. አላህንና መልዕክተኛውን ሙሐመድን (ﷺ) ለመወንጀል በሚደደረጉ ስብሰባዎች ላይ መገኘት ተገቢ አለመሆኑን፤
10. የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢደበቅ ከአላህ መሰወር እንደማይችል፤

11. የአላህ ቁጣና መአት የወረደባቸውን አይሁድን ወዳጅ ከማድረግ መቆጠብ እንዳለብና በኢስላም ቅርብ ስጋ ዘመድም ቢሆን ከሃዲን ወዳጅ ማድረግ ክልክል መሆኑን፤
12. ይህ ጉዳይ ሙስሊሞች በህይወታቸው ከሚፈተኑባቸው ነገሮች ውስጥ ዋነኛ መሆኑን፤
13. በግዴታ ነገሮች አላህን ቀጥ ብሎ መገዛት ከጥቃቅን ነገሮች የሚሸፍን መሆኑን፤
14. በውሸት መማል ስለ መከልከሉ የተቀመጠው ነጥብ፤ ውሸታም ለሰዎች አልፎ በአላህ ዘንድ ምንም ቦታ እንደሌላቸውና በውሸታቸው ሰዎችን ቢያልፉም ከአላህ ቅጣት ግን መዳን እንደማይችሉ፤
15. ሰይጣን የራሱ ቡድን እንዳለው የሱ የሆኑ ቡድኖች ሁሉ ከሳሪዎች መሆናቸውን፤
16. ሰይጣን የሰውን ልጆች ከመቆጣጠሩ ምልክቶች መካከል በልቡም ሆነ በምላሱ አላህን አለማንሳቱ፤ በተግባሩም ሆነ በአንደበቱ አላህን ቃልና ዛቻውን አለማስታወሱ መሆናቸውን እንረዳለን።

በአላህ ፈቃድ የተከራካሪዋ ሴት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

ምዕራፍ (59)
# የማስወጣት ምዕራፍ
(ሱረቱ አል ሐሽር)

سُورَةُ الحَشۡرِ

በመዲና የወረደ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (24) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

سَبَّحَ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ١

1. በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ አላህን አሞገሰ (አጠራ)። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

ከማስወጣት ምዕራፉ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ በኒ ነዲሮች ከተባሉ ከአይሁድ ነገዶች ጋር ወደው እና ከእሳቸው ጋርም ሀገርን በማስከበር ላይ ሊዋጉ ተስማምተው ነበር። ነብዩ (ﷺ) ከመካ ሰወች ጋር ጋር ባደረጉት የበድር ዘመቻ ጦርነት የበላይነታቸውን ሲያረጋግጡ በኒ ነዲሮች ይህ ሰውማ እውነትም በተውራት የተነገረለት ነብይ ነው ማለት ነው። በማለት ተቀበለው ሳሉ በኡሁድ ዘመቻ ላይ ሙስሊሞች ሲሸነፉና ጥቃት ሲደርስባቸው በኒ ነዲሮች አቋማቸውን ቀይረው ቃላቸውን አፍርሰው በሙስሊሞች ጠላትነታቸውን በይፋ አወጁ። በዚህ ጊዜ ነበር ቀያቸውን ከበው እንዲለቁ አሳምነው የታረቋቸው። (ሱዩጢ)

هُوَ ٱلَّذِيٓ أَخۡرَجَ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ مِن دِيَٰرِهِمۡ لِأَوَّلِ ٱلۡحَشۡرِۚ مَا ظَنَنتُمۡ
أَن يَخۡرُجُواْۖ وَظَنُّوٓاْ أَنَّهُم مَّانِعَتُهُمۡ حُصُونُهُم مِّنَ ٱللَّهِ فَأَتَىٰهُمُ ٱللَّهُ مِنۡ حَيۡثُ لَمۡ يَحۡتَسِبُواْۖ
وَقَذَفَ فِي قُلُوبِهِمُ ٱلرُّعۡبَۚ يُخۡرِبُونَ بُيُوتَهُم بِأَيۡدِيهِمۡ وَأَيۡدِي ٱلۡمُؤۡمِنِينَ فَٱعۡتَبِرُواْ يَٰٓأُوْلِي
ٱلۡأَبۡصَٰرِ ٢ وَلَوۡلَآ أَن كَتَبَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِمُ ٱلۡجَلَآءَ لَعَذَّبَهُمۡ فِي ٱلدُّنۡيَاۖ وَلَهُمۡ فِي ٱلۡأٓخِرَةِ عَذَابُ
ٱلنَّارِ ٣ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ شَآقُّواْ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥۖ وَمَن يُشَآقِّ ٱللَّهَ فَإِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلۡعِقَابِ ٤

2-4. እርሱ ያ ከመጽሐፍ ሰዎች መካከል እነዚያን በአላህ የካዱትን ወገኖች ከቤቶቻቸው የመጀመሪያውን ማስወጣት ያስወጣቸው ነው። (ሙስሊሞች ሆይ!) መውጣታቸውንም አላሰባችሁትም ነበር። እነርሱም ምሽጎቻቸው ከአላህ ኃይል የሚከላከሉላቸው መሆናቸውን አሰቡ። አላህ ግን ካላሰቡት በኩል መጣባቸው*። እናም በልቦቻቸው ውስጥ መርበድበድን (ፍርሃትን)

ጣለባቸው። ቤቶቻቸውን በገዛ እጆቻቸውና በአማኞች እጅ ያፈርሳሉ (አፈረሱ)። እናንተ የአእምሮ ባለቤቶች ሆይ፣ አስተውሉ። በእነርሱም ላይ አላህ ከአገር መውጣትን ባልፈረደ ኖሮ በቅርቢቱ ዓለም በቀጣቸው ነበር። ለእነርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም የእሳት ቅጣት አለባቸው። ይህ እነርሱ አላህንና መልዕክተኛውን በመከራከራቸው ምክንያት ነው። አላህን የሚከራከር ሰው ሁሉ (ይቀጣዋል) አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና።

✷ ይኸውም ነብዩ እንዲዘምቱባቸው በማድረጉ ሲሆን ጉዳዩ እዚህ ላይ ይደርሳል ብለው አላሰቡም ነበር። ቢሞከርም አቅማቸው ከፍተኛ ነው ብለው ያምኑ ነበር።

مَا قَطَعْتُم مِّن لِّينَةٍ أَوْ تَرَكْتُمُوهَا قَآئِمَةً عَلَىٰٓ أُصُولِهَا فَبِإِذْنِ ٱللَّهِ وَلِيُخْزِيَ ٱلْفَٰسِقِينَ ٥
وَمَآ أَفَآءَ ٱللَّهُ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ مِنْهُمْ فَمَآ أَوْجَفْتُمْ عَلَيْهِ مِنْ خَيْلٍ وَلَا رِكَابٍ وَلَٰكِنَّ ٱللَّهَ
يُسَلِّطُ رُسُلَهُۥ عَلَىٰ مَن يَشَآءُ ۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَيْءٍ قَدِيرٌ ٦

5-6. ከዘንባባ (ከተምር ዛፍ) ማንኛዋም የቆረጣችኋት ወይም በግንዶቿ ላይ የቆመች ሆና የተዋችኋት ሁሉ በአላህ ፈቃድ ነው። አመፀኞችን ያዋርድ ዘንድ (መቁረጥን ፈቀደ)። ከእነርሱም ገንዘብ ወደ መልዕክተኛው አላህ የመለሰውን በእርሱ ላይ ፈረሶችንና ግመሎችን አላስጋለባችሁበትም። ግን አላህ መልዕክተኞቹን በሚሻው ሰው ላይ ይሾማል። አላህ ሁሉ ነገር ላይ ቻይ ነውና።

ከማስወጣት ምዕራፍ (5) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ነብዩ (ﷺ) በኒ ነዲሮችን በከበቡ ጊዜ እጅ አልሰጥ ሲሉ ተምሮቻቸውን እንዲቆርጡባቸው ሲያዙና ሲተገብሩ ሙሐመድ ሆይ! ይህን መሰል የጥፋት ተግባር ውግዝ አልነበረም እንዴ? ዛሬ እንዴት ፈቀድክ? በማለት ሲጠይቋቸው ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

مَّآ أَفَآءَ ٱللَّهُ عَلَىٰ رَسُولِهِۦ مِنْ أَهْلِ ٱلْقُرَىٰ فَلِلَّهِ وَلِلرَّسُولِ وَلِذِى ٱلْقُرْبَىٰ وَٱلْيَتَٰمَىٰ
وَٱلْمَسَٰكِينِ وَٱبْنِ ٱلسَّبِيلِ كَىْ لَا يَكُونَ دُولَةًۢ بَيْنَ ٱلْأَغْنِيَآءِ مِنكُمْ ۚ وَمَآ ءَاتَىٰكُمُ
ٱلرَّسُولُ فَخُذُوهُ وَمَا نَهَىٰكُمْ عَنْهُ فَٱنتَهُوا۟ ۚ وَٱتَّقُوا۟ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ شَدِيدُ ٱلْعِقَابِ ٧

7. አላህ ከከተሞች ሰዎች ሀብት መካከል በመልዕክተኛው ላይ የመለሰው ሀብት ከናንተ ውስጥ በሀብታሞች መካከል ተዘዋዋሪ እንዳይሆን ለአላህና ለመልዕክተኛው፣ ለዝምድና ባለቤትም፣ አባት ለሌላቸው የቲም ልጆችም፣ ለድሆችና፣ ለመንገደኛ፤ የሚስሰጥ ነው። መልዕክተኛው የሰጣችሁን ሁሉ ማንኛውም ነገር ያዙት። ከእርሱ የከለከላችሁን ነገር ሁሉም ተከልከሉ።✷ አላህን ፍሩ። አላህ ቅጣተ ብርቱ ነውና።

✴ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐል ቀማህ እንዳስተላለፉት ዐብደላህ ኢብኑ መስዑድ እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ንቅሳት የሚነቅሱትንና የሚነቀሱትን፤ የቅንድባቸውን ፀጉር የሚላጩትን፤ ጥርሶቻቸውን ለውበት ሲሉ የሚነቀሱትን፤ የአላህን ተፈጥሮ በራሳቸው የሚቀይሩትን ሴቶች ረገረሟቸዋል።» ይህ ወሬ ኡሙ የዕቁብ የምትባል ከበኒ አሰድ ጎሳ የሆነች ሴት ይደርስና ወደርሳቸው መጥታ፡- «አከሌን አከሌን እንደረገምክ በእርግጥ ደርሶኛል» አለቻቸው። እሳቸውም፡- «የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (ﷺ) የረገማቸውንና በአላህ ቁርኣን ውስጥ የተረገሙትን እንዴት አልረግማቸውም?» አሉ። ሴትየዋም «በሁለቱ ሎኾች ላይ የተፃፉትን አንብቤያ ቸዋለሁ ነገር ግን አንተ የምትለውን አላገኘሁም» አለቻቸው። እሳቸውም «በእርግጥ በትክክል ብታነቢያቸው ኖሮ ታገኚው ነበር። እንደው «መልዕክተኛውም የሰጣችሁን ማንኛውም ነገር ያዙት። ከርሱም የከለከላቸውን ነገር ተከልከሉ» (አል ሐሽር፡ 7) የሚለው አላነበብሽምን?» አሏት። እሷም «እንዴታ! አንብቤዋለሁ እንጂ» አለቻቸው። እሳቸውም «በእርግጥ እሳቸው ከዚህ ነገር ከልክለዋል» አሏት። እሷም «ቤተሰቦችህ ይህን ሲፈፅሙ በእርግጥ ተመልክቻቸዋለሁ» አለቻቸው። እሳቸውም «ሂጂና ተመልከቺያቸው» አሏት። ሴትየዋም ሄዳ ስትመለከት የምትፈልገውን ነገር ሳትመለከት ቀረች። እሳቸውም «ሚስቴ አንቺ እንደምታ ስቢው ሆና በነበር አብሬ አልኖርም ነበር» አሏት። (ቡኻሪ ዘግበውታል)

ዐብደላህ ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ)፡- «ሰው ሰራሽ የሆነ ፀጉር የምትጠቀምን ሴት ረግመዋል» ብለዋል።

لِلْفُقَرَآءِ ٱلْمُهَٰجِرِينَ ٱلَّذِينَ أُخْرِجُوا۟ مِن دِيَٰرِهِمْ وَأَمْوَٰلِهِمْ يَبْتَغُونَ فَضْلًا مِّنَ ٱللَّهِ وَرِضْوَٰنًا
وَيَنصُرُونَ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥٓ ۚ أُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلصَّٰدِقُونَ ﴿٨﴾ وَٱلَّذِينَ تَبَوَّءُو ٱلدَّارَ وَٱلْإِيمَٰنَ مِن
قَبْلِهِمْ يُحِبُّونَ مَنْ هَاجَرَ إِلَيْهِمْ وَلَا يَجِدُونَ فِى صُدُورِهِمْ حَاجَةً مِّمَّآ أُوتُوا۟ وَيُؤْثِرُونَ
عَلَىٰٓ أَنفُسِهِمْ وَلَوْ كَانَ بِهِمْ خَصَاصَةٌ ۚ وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفْسِهِۦ فَأُو۟لَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْمُفْلِحُونَ ﴿٩﴾
وَٱلَّذِينَ جَآءُو مِنۢ بَعْدِهِمْ يَقُولُونَ رَبَّنَا ٱغْفِرْ لَنَا وَلِإِخْوَٰنِنَا ٱلَّذِينَ سَبَقُونَا بِٱلْإِيمَٰنِ
وَلَا تَجْعَلْ فِى قُلُوبِنَا غِلًّا لِّلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ رَبَّنَآ إِنَّكَ رَءُوفٌ رَّحِيمٌ ﴿١٠﴾

**8-10.** ለእነዚያ የአላህን ችሮታና ውዴታውን የሚፈልጉና አላህንና መልዕክተኛውን የሚረዱ ሆነው ከአገሮቻቸውና ከገንዘቦቻቸው ለተወጡ (ለተባረሩ) ስደተኞች ድሆች ይሰሰጣል። እነዚያ እነርሱ እውነተኞች ናቸው። እነዚያም ከበፊታቸው ሀገሪቱን መዲና መኖሪያ ያደረጓትና እምነት በልባቸው የሰረፀባቸው ወደ እነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ። ስደተኞችም ከተሰጡት ነገር ላይ በልቦቻቸው ውስጥ እንኳን ምንም ቅሬታን አያሳድሩም። በእነርሱ ላይ ችግር ቢኖርባቸቸውም እንኳ በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ያስቀድማሉ።[*1] ከነፍሶቻቸው ንፉግነት[*2] የሚጠብቁ ሰዎች ሁሉ እነዚያ የተሳካለቸውና ምኞታቸውን አግኚዎች ማለት እነርሱ ብቻ ናቸው። እነዚያም ከበኋላቸው የመጡት ጌታችን ሆይ፣ ለእኛም ለእነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምህረት አድርግ። በልቦቻችንም ውስጥ ለእነዚያ ለአመኑት ሰዎች ሁሉ ጥላቻን አታድርግ። ጌታችን ሆይ፣ አንተ ሩህሩህ; አዛኝ ነህና ይላሉ።

✳1 ከዚህ ላይ አያሌ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል። ከእነዚህ ወርቃማ ምሳሌዎች መካከል፡

1. ያ! በታሪክ መሰሉ ተሰርቶ የማያውቀው ታሪክ ነው።
ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዲህ አሉ። «ዐብዱረህማን ኢብኑዐውፍ መዲና ሲመጡ ከሰዕድ ኢብኑረቢዕ ጋር ወንድማመች አደረጓቸው። ሰዕድ ገንዘቡ ብዙ ስለነበረ ገነዘቤን ለሁለት ከፍየ ግማሹን እሰጥሃለሁ። ሁለት ሚስቶችም ስላሉኝ ደስ ያለችህን ነገረኛና ፈትቻልህ ዒዳዋን ስትጨርስ ታገባታለህ አለው። ዐብዱረህማን ግን ገንዘብህንም ሆነ ቤተሰብህን በረካ ያደርግልህ ለእኔ ግን ገበያዉን አሳየን ብቻ አለው።

2. ቀይስ ኢብኑ ሰዕድ የተባለ አንድ ቸር ሀብታም ነበር። በጠና ታመመና ብዘዎች የእሱ ብድር ስላለባቸው ከመዘየር ተቆጠቡና ሲጠይቅ ብድርክን ስላልከፈሉህ ነው ብዙዎች የማይመጡት ተባለ። በዚህ ግዜ ወንድሞቸን ከመዘየር የሚያስከለክል ገንዝብ ምን ገንዘብ ይባላል፣ አለና አንድን ሰው ጠርቶ የቀይስ ብድር ያለበት ሁሉ ከዛሬ ጀምሮ ነፃ አድረጓችኋል ብሎ እንዲለፍፍ አዘዘና ሲለፍፍ በዚያው ዕለት ከጠያቂዎች ብዛት ወደርሱ የሚወጡበት ደረጃው ፈረሰ»

3. በቃዲሲያ ጦርነት ላይ ቆስለው ከነበሩት ሙስሊሞች መካከል ዒክሪመት ኢብኑ አቢ ጀህል ለሞት እያጣጣረ ባለበት ውሃ አምጥተዎለት ለሌላው ወንድሙ ለህሪስ ኢብኑ ሂሻም እንዲሰጠው አዘ እርሱም ለሌላው እንዲሰጥ እያደረገ። አንዱ ለሌላይ ጠጣው እየተባባሉ አንዱም ሳይጠጣው የሁሉም ሩሃቸው ወጣች ተብሎ የተዘገበው ነው።

✳2 ንፉግነት ማለት ራስ ወዳድነት፣ ተገቢን አለመስጠት፣ የሌላን ንብረት መውሰድ፣ ሊባል ይችላል። ንፉግነት በሌላ ጉዳይም ላይ የሚከሰት ቢሆንም በይበልጥ የሚታየው በገንዘብ ላይ በመሆኑ በዚህም ሆነ በተጋቡን ላይ ከገንዘብ ጋር በተያያዘ ነው የተወሳው።

ከማስወጣት ምዕራፉ (9) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- (ሀ) የመዲና አንሷሮች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ለሙሐጅር ወንድሞቻችን መሬዎቻችን በእኩል ከፈሉልን ብለው ጥያቄ ሲያቀርቡና ነብዩ (ﷺ) ነገሩ እንዲህ ሳይሆን እነሱ ጉልበት ሁነው እናንተ መሬት ሁናችሁ እኩል ተካፈሉ በማለት ሲነግሯቸው ሀሳቡን ተቀብለናል በማለታቸው ነው። (ዋሒዲ)

۞ أَلَمْ تَرَ إِلَى ٱلَّذِينَ نَافَقُوا۟ يَقُولُونَ لِإِخْوَٰنِهِمُ ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ مِنْ أَهْلِ ٱلْكِتَٰبِ لَئِنْ
أُخْرِجْتُمْ لَنَخْرُجَنَّ مَعَكُمْ وَلَا نُطِيعُ فِيكُمْ أَحَدًا أَبَدًا وَإِن قُوتِلْتُمْ لَنَنصُرَنَّكُمْ وَٱللَّهُ
يَشْهَدُ إِنَّهُمْ لَكَٰذِبُونَ ﴿١١﴾ لَئِنْ أُخْرِجُوا۟ لَا يَخْرُجُونَ مَعَهُمْ وَلَئِن قُوتِلُوا۟ لَا يَنصُرُونَهُمْ
وَلَئِن نَّصَرُوهُمْ لَيُوَلُّنَّ ٱلْأَدْبَٰرَ ثُمَّ لَا يُنصَرُونَ ﴿١٢﴾

**11-12.** እነዚያን ወደ ንፍቅና የገቡትን አላወከምን? ከመጽሐፍ ሰዎች መካከል ለእነዚያ ለካዱት✳ ወንድሞቻቸው ከአገር ብትባርሩ አብረናችሁ እንወጣለን። በእናንተ ጉዳይ አንድንም ሰው በፍፁም ሁልጊዜም አንታዘዝም። ጦርነት ቢታወጅባችሁም በእርግጥ እንረዳችኋለን ይሏቸዋል። አላህም እነርሱ ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል። ቢባረሩም አብረዋቸው አይባረሩም። ቢገደሉም (ቢወጉም) ቢዘመትባቸውም አይረዱዋቸውም። ቢረዷቸውም ለሽሽት ጀርባዎችን ያዞራሉ። ከዚያ እርዳታን አያገኙም።

✷ ነብዩ (ﷺ) ወደ መዲና በሄዱ ጊዜ በኒ ነዲሮች የተባሉት ነገዶች ላይ ወደውና ከሳቸውም ጋር ሀገርን ለማስከበር ላይዋጉ ተስማምተው ነበር። ታዲያ ነብዩ (ﷺ) ከመኮች ጋር ባደረጉት የበድር ዘመቻ ጦርነት የበላይነታቸውን ሲያረጋግጡ በኒ ነዲሮች ይህ ሰውማ እውነትም በተውራቱ የተነገረለት ነብይ ነው በማለት ተቀብለው ሳሉ በኡሁድ ዘመቻ ላይ ሙስሊሞች ሲሸነፉና ጥቃት ሲደርስባቸው በኒ ነዲሮች አቋማቸውን ቀይረውና ቃላቸውን አፍርሰው ለሙስሊሞች ጠላትነታቸውን በይፋ አወጁ። በዚህ ጊዜ ነበር ስራቸውን ከበው እንዲለቁ አሳምነው የራቋቸው። አቡ ዳውድ ኢብኑ ከሲርና ሲዩጢ።

ከማስወጣት ምዕራፍ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ የበኒ ቁረይዟ አይሁዳ ኢስላምን ተቀብለናል ብለው የነበሩትና ለበኒ ነዲሮች ደግሞ ከተባረራችሁ እኛም አብረን እንሰደዳለን ይሉ ስለነበር ነው። (ሱዩጢ)

لَأَنتُمْ أَشَدُّ رَهْبَةً فِي صُدُورِهِم مِّنَ ٱللَّهِۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَوْمٌ لَّا يَفْقَهُونَ ﴿١٣﴾ لَا يُقَٰتِلُونَكُمْ جَمِيعًا إِلَّا فِي قُرًى مُّحَصَّنَةٍ أَوْ مِن وَرَآءِ جُدُرٍۭۚ بَأْسُهُم بَيْنَهُمْ شَدِيدٌۚ تَحْسَبُهُمْ جَمِيعًا وَقُلُوبُهُمْ شَتَّىٰۚ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمْ قَوْمٌ لَّا يَعْقِلُونَ ﴿١٤﴾

**13-14.** (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ!) እናንተ በልቦቻቸው ውስጥ በማስፈራት ከአላህ ይልቅ የበረታችሁ (የከበዳችሁ) ናችሁ። ይህም የሆነው እነርሱ የማያውቁ ህዝቦች በመሆናቸው ነው። በተመሸጉ ከተሞች ውስጥ ወይም ከአጥሮች በስተጀርባ ሆነው እንጂ የተሰበሰቡ ሆነው አይዋጉዋችሁም። ኃይላቸው በመካከላቸው ብርቱ ነው። ልቦቻቸው የተበታተኑ ሲሆን የተሰበሰቡ ናቸው ብለህ ትጠራጠራቸዋለህ (አንድ ይመስሉሃል)። ይህ እነርሱ አእምሮ የሌላቸው ህዝቦች በመሆናቸው ነው።

كَمَثَلِ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ قَرِيبًاۖ ذَاقُواْ وَبَالَ أَمْرِهِمْ وَلَهُمْ عَذَابٌ أَلِيمٌ ﴿١٥﴾ كَمَثَلِ ٱلشَّيْطَٰنِ إِذْ قَالَ لِلْإِنسَٰنِ ٱكْفُرْ فَلَمَّا كَفَرَ قَالَ إِنِّي بَرِيٓءٌ مِّنكَ إِنِّيٓ أَخَافُ ٱللَّهَ رَبَّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿١٦﴾

**15-16.** ብጤያቸው ልክ እንደነዚያ ከእነርሱ በፊት በቅርብ ጊዜ የተግባራቸውን ቅጣት እንደቀመሱት ወገኖች ብጤ ነው። ለእነርሱም አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። ምሳሌያቸው ልክ እንደዚያ ሰውን በአላህ ካድ ብሎ ሰውየው በካደ ጊዜ እኔ ከአንተ ንፁህ ነኝ እኔ የዓለማትን ጌታ አላህን እፈራለሁ እንዳለው ሰይጣን ነው።

فَكَانَ عَٰقِبَتَهُمَآ أَنَّهُمَا فِي ٱلنَّارِ خَٰلِدَيْنِ فِيهَاۚ وَذَٰلِكَ جَزَٰٓؤُاْ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿١٧﴾

**17.** የሁለቱም መጨረሻቸው እነርሱ በውስጡ ዘወታሪዎች ሲሆኑ በእሳት ውስጥ መሆን ነው። ይህም ቅጣት የበዳዩች ሁሉ ዋጋ ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ ٱتَّقُواْ ٱللَّهَ وَلۡتَنظُرۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ لِغَدٖۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَۚ
إِنَّ ٱللَّهَ خَبِيرُۢ بِمَا تَعۡمَلُونَ ١٨ وَلَا تَكُونُواْ كَٱلَّذِينَ نَسُواْ ٱللَّهَ فَأَنسَىٰهُمۡ أَنفُسَهُمۡۚ
أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡفَٰسِقُونَ ١٩

**18-19.** እናንተ በትክክል በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህን በትክክል ፍሩ። ማንኛይቱም ነፍስ ለነገ ያስቀደመችውን ትመልከት፤ አላህን በትክክል ፍሩ፤ አላህ በምትሰሩት ነገር ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና። እንደ እነዚያ አላህን እንደረሱትና ነፍሶቻቸውን እንዳስረሳቸው ሰዎች አትሁኑ። እነዚያ እነርሱ አመፀኞች ናቸው።

لَا يَسۡتَوِيٓ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِ وَأَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِۚ أَصۡحَٰبُ ٱلۡجَنَّةِ هُمُ ٱلۡفَآئِزُونَ ٢٠

**20.** የእሳት ጓዶችና የገነት ጓዶች እኩል አይሆኑም። የገነት ጓዶች ምኞታቸውን አግኚዎች ናቸውና።

لَوۡ أَنزَلۡنَا هَٰذَا ٱلۡقُرۡءَانَ عَلَىٰ جَبَلٖ لَّرَأَيۡتَهُۥ خَٰشِعٗا مُّتَصَدِّعٗا مِّنۡ خَشۡيَةِ ٱللَّهِۚ
وَتِلۡكَ ٱلۡأَمۡثَٰلُ نَضۡرِبُهَا لِلنَّاسِ لَعَلَّهُمۡ يَتَفَكَّرُونَ ٢١

**21.** (ሙሐመድ ሆይ)፣ ይህንን ቁርኣን በተራራ ላይ ባወረድነው ኖሮ ከአላህ ፍራቻ የተነሳ ተዋራጅና ተሰንጣቂ ሆኖ ባየኸው ነበር።* እነዚህን ምሳሌዎች ለሰዎች ያስተነትኑ ዘንድ እንገልፃቸዋለን።

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ጃቢር ኢብኑ ዐብደላህ እንዳስተላፉት፡- «የጁመዓ ኹጥባህ በሚደረግበት ጊዜ የተምር ዛፍ ግንድ ላይ ይቆሙ ነበር። አንድ ጊዜ ከአንሷር ጎሳ የሆነ ሰው ወይም የሆነች ሴት «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሚንበር እንስራልዎትን?» አለ ወይም አለች። እሳቸውም «ከፈለጋችሁ» አሏቸው። ሚንበር ሰሩላቸው። በጁምዓህ እለት ወደ አዲሱ ሚንበር ሲሄዱ የቴምር ዛፍ ግንድ ልክ እንደ ሕፃን ጮኸ። ነብዩ (ﷺ) ከሚንበራቸው ወርደው ወደርሱ በመሄድ አቀፉት። ግንዱም ልክ ሕፃን ልጅ እንደሚያለቅሰው እያለቀሰ ቀስ በቀስ ለቅሶውን እያቆመ ሄደ። ይህን ጊዜም «በእርሱ ቅርበት ይሰማው የነበረውን ዚክር (ሃይማኖታዊ ትምህርት) በማጣቱ ነው የሚያለቅሰው።» አሉ።

هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِي لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۖ عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِۖ هُوَ ٱلرَّحۡمَٰنُ ٱلرَّحِيمُ ٢٢

**22.** እርሱ ያ፣ አላህ ነው። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፤ ሩቁንና ቅርቡን አዋቂ የሆነ ነው። እርሱ እጅግ በጣም ሩህሩህ፤ በጣም አዛኝ ነው።

هُوَ ٱللَّهُ ٱلَّذِى لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ ٱلۡمَلِكُ ٱلۡقُدُّوسُ ٱلسَّلَٰمُ ٱلۡمُؤۡمِنُ ٱلۡمُهَيۡمِنُ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡجَبَّارُ ٱلۡمُتَكَبِّرُۚ سُبۡحَٰنَ ٱللَّهِ عَمَّا يُشۡرِكُونَ ﴿٢٣﴾

**23.** እርሱ ያ! አላህ ነው። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ የሌለ፣ ንጉሱ፣ ከጎደሎ ሁሉ የጠራ፣ የሰላም ባለቤት፣ ፀጥታን ሰጪ፣ ባሮቹን ጠባቂ፣ አሸናፊ፣ ኃያልና ኩሩ ነው። አላህ ከሚያጋሩት ሁሉ የጠራ ነው።

هُوَ ٱللَّهُ ٱلۡخَٰلِقُ ٱلۡبَارِئُ ٱلۡمُصَوِّرُۖ لَهُ ٱلۡأَسۡمَآءُ ٱلۡحُسۡنَىٰۚ يُسَبِّحُ لَهُۥ مَا فِى ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِۖ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ﴿٢٤﴾

**24.** እርሱ አላህ ፈጣሪ፤ (ከኢምንት) አስገኚ፤ ቅርፅን አሳማሪ ነው። ለእርሱ መልካሞች ስሞች አሉት። በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ እርሱን ያሞግሳል። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

**ከነዚህ አንቀጾች ከምናገኛቸው ዋና ዋና ነጥቦች፡-**

1. አላህን ማክበርና ማሞገስ፤
2. ከከሓዲያን ያለ ጦርነት የሚወሰዱ ገንዘቦች ምንነት፤
3. እኒያ ከአይሁድ ጋር በሙስሊሞች ላይ የተባበሩ መናፍቃንን ማጋለጥ፤
4. የቁርኣንን ትልቅነት ተፅዕኖ በመግለፅ ያጠቃልላል።
5. የአላህ ስሞች የተወሰኑትን መዘርዘር።

በአላህ ፈቃድ የማስወጣት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (60)
## (የፈታኟ) የሞካሪዋ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ሙምተሒነህ)

سُورَةُ المُمتَحنَةِ

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (13) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَّخِذُواْ عَدُوِّي وَعَدُوَّكُمۡ أَوۡلِيَآءَ تُلۡقُونَ إِلَيۡهِم بِٱلۡمَوَدَّةِ وَقَدۡ
كَفَرُواْ بِمَا جَآءَكُم مِّنَ ٱلۡحَقِّ يُخۡرِجُونَ ٱلرَّسُولَ وَإِيَّاكُمۡ أَن تُؤۡمِنُواْ بِٱللَّهِ رَبِّكُمۡ إِن كُنتُمۡ
خَرَجۡتُمۡ جِهَٰدٗا فِي سَبِيلِي وَٱبۡتِغَآءَ مَرۡضَاتِيۚ تُسِرُّونَ إِلَيۡهِم بِٱلۡمَوَدَّةِ وَأَنَا۠ أَعۡلَمُ بِمَآ أَخۡفَيۡتُمۡ وَمَآ
أَعۡلَنتُمۡۚ وَمَن يَفۡعَلۡهُ مِنكُمۡ فَقَدۡ ضَلَّ سَوَآءَ ٱلسَّبِيلِ ١ إِن يَثۡقَفُوكُمۡ يَكُونُواْ لَكُمۡ أَعۡدَآءٗ
وَيَبۡسُطُوٓاْ إِلَيۡكُمۡ أَيۡدِيَهُمۡ وَأَلۡسِنَتَهُم بِٱلسُّوٓءِ وَوَدُّواْ لَوۡ تَكۡفُرُونَ ٢

**1-2.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ጠላቶቼንና ጠላቶቻችሁን ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዙ። የመጣላችሁን ትክክለኛ ሃይማኖት የካዱ ሲሆኑ ውዴታን ለእነርሱ ታደርጋላችሁ። መልዕክተኛውና እናንተን በጌታችሁ በአላህ ስላመናችሁ ብቻ ከሀገራችሁ ያወጣሉ በመንገዴ ለመታገልና ውዴታየን ለመፈለግ የወጣችሁ እንደሆናችሁ እነርሱን (ወዳጆች አድርጋችሁ አትያዟቸው)። እኔ የምትደብቁትንና የምትገልፁትን ሁሉ የማውቅ ስሆን ከእነርሱ ጋር ፍቅር ትመሳጠራላችሁ። ከናንተ መካከልም ይህንን ሚፈፅም ሰው ቀጥተኛውን መንገድ በእርግጥ ስቷል። ቢያሸንፏችሁ (ቢያገኟችሁ) ለእናንተ ጠላቶች ይሆናሉ። እጆቻቸውና ምላሶቻቸውንም ወደ እናንተ በክፉ ይዘረጋሉ። ብትክዱም ተመኙ።

لَن تَنفَعَكُمۡ أَرۡحَامُكُمۡ وَلَآ أَوۡلَٰدُكُمۡۚ يَوۡمَ ٱلۡقِيَٰمَةِ يَفۡصِلُ بَيۡنَكُمۡۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٞ ٣

**3.** ዘመዶቻችሁም ሆኑ ልጆቻችሁ በትንሳኤ ቀን አይጠቅሟችሁም። አላህ በትንሳኤ ቀን በመካከላችሁ ብይን በመስጠት ይለያል። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና።

የሞካሪዋ ምዕራፍ ከ (1-3) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ይህን ጉዳይ በተመለከተ ብዙ የተወሩ ዘገባዎች ቢኖሩም ብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ያገኘው ከዚህ ቀጥሎ የተወሳው ምክኒያት ነው። ይኸዉም ሀጢብ ቢን አቢ በልተዓህ በተባለ ሶሀብይ ምክንያት ነው። ታሪኩ በአጭሩ ሳራህ የተባለች አንዲት ሴት ከመዲና ወደ መካ እንደምትሄድ ያወቀው ይህ ሶሀብይ ነብዩ (ﷺ) በመኮች ላይ ሊዘምቱባቸው እንዳሰቡና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የሚገልፅ ደብዳቤ ፅፎላቸው ሳለ ጅብሪል ከሰማይ ወረደ። ለነብዩ (ﷺ) ድርጊቱን በዝርዝር ነገራቸውና ዓሊይን፤ ዓማርን፤ ዙበይርን፤ ጦልሃን፤ ሚቅዳድንና አቡ መርሰድን ደብዳቤውን ይዛ በመጓዝ ላይ ያለችውን ሴት ወደ ምትገኝበት ቦታ ሄደው መልዕክቱን አንዲያመጡት አዘዟቸው። በተባለው ቦታም ሴትዮዋን አግኝተው ስለ ደብዳቤው ሲጠይቋት በፍፁም አልያዝኩም ስትል ማለች። እነርሱ ግን ዕቃዋን ፈትሸው ሲያጡ ሊመለሱ ሲያስቡ ዓልይ ተነሱና ዋሽተንም ተዋሽተንም አናውቅም በማለት ሰይፋቸውን አውጥተው ፁሑፍን አምጪ አለበለዚያ አንገትሽን ነው የምቆርጠው ሰለሏትና ማምረራቸውን ስታውቅ ከቁንጮዋ (ሹሩባዋ) አውጥታ ሰጠቻቸው። እነሱም እሷን ለቀው ጹሑፉን ይዘው ወደ ነብዩ (ﷺ) መጡ።

ነብዩም (ﷺ) ሃጢብን በማስጠራት ይህን ጹሑፍ ታውቀዋለህን? ሲሉት አዋ አለ። ምን ሆነህ ነው ለዚህ ጥፋት የበቃኸው? ሲሉት በጌታየ ይህንብኝ ከሰለምኩኝ አንድም ቀን አልከፈርኩም። አንድ ቀን አታልየ አላውቅም። እነሱንም ከተለየኋቸው ጀምሮ ወዳጃቸውን አላውቅም። ነገር ግን ከሙሐጅሮች ውስጥ በመካ ጠንካራ ዘመድ የሌለው ያለ እኔ ምንም የለ። እኔ ግን ባዕድ ነኝና ለቤተሰቦቼ ፈርቼ ከነሱ ዘንድ ውለታ ያስቆጠርልኝ መስሎኝ ነው። አላህ በእነርሱ ላይ ቁጣውን እንደሚያወርድ እጠብቃለሁኝና የእኔ ጹሁፍ ምንም አይጠቅማቸውም በማለት ምክንያቱን ሲያቀርብ ነበዩ አዎ እውነቱን ነው በማለት ምክንያቱን ተቀበሉት። በዘህ ጊዜ ዑመር ይህን አስመሳዮች እንግደለው ይፈቀድልኝ ቢሉም ነብዩም ከበድር ሰዎች አንዱ ነው። ስለ በድር ሰዎች አላህ ከበድር በኋላ የፈለጉትን ቢሰሩ ምሬአቸዋለሁ ብሎ ከሆነ የምታውቀው ነገር አለህን? በማለት ከለከሉት። በዚህ ጊዜ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

እናም ይህ አንቀፅ ከከሓዲያን ጋር መተዳደር እንጅ በምንም አይነት ቢሆን መወዳጀትን ይከለክላል።

قَدْ كَانَتْ لَكُمْ أُسْوَةٌ حَسَنَةٌ فِىٓ إِبْرَٰهِيمَ وَٱلَّذِينَ مَعَهُۥٓ إِذْ قَالُوا۟ لِقَوْمِهِمْ إِنَّا بُرَءَٰٓؤُا۟ مِنكُمْ وَمِمَّا تَعْبُدُونَ مِن دُونِ ٱللَّهِ كَفَرْنَا بِكُمْ وَبَدَا بَيْنَنَا وَبَيْنَكُمُ ٱلْعَدَٰوَةُ وَٱلْبَغْضَآءُ أَبَدًا حَتَّىٰ تُؤْمِنُوا۟ بِٱللَّهِ وَحْدَهُۥٓ إِلَّا قَوْلَ إِبْرَٰهِيمَ لِأَبِيهِ لَأَسْتَغْفِرَنَّ لَكَ وَمَآ أَمْلِكُ لَكَ مِنَ ٱللَّهِ مِن شَىْءٍ ۖ رَّبَّنَا عَلَيْكَ تَوَكَّلْنَا وَإِلَيْكَ أَنَبْنَا وَإِلَيْكَ ٱلْمَصِيرُ ﴿٤﴾

**4.** ኢብራሂምና እነዚያ ከእርሱ ጋር አብረው በነበሩት (ምዕመናን) ለእናንተ መልካም አርአያ አለላችሁ*። ይኸዉም ለህዝቦቻቸው እኛ ከናንተና ከዚያ ከአላህ ሌላ ከምትገዙት ጣዖታት ሁሉ ንፁሆች ነን። በእናንተም ካድን። በአላህ አንድ ብቻ ሲሆን እስከምታምኑ ድረስ በእኛና በእናንተ መካከል ጠብና ጥላቻ ዘወትር ተገለፀ። ባሉ ጊዜ (መልካም መከተል አለላችሁ) ኢብራሂም ለአባቱ፡- ለአንተ ከአላህ ቅጣት ምንም የማልጠቅምህ (የማላድንህ) ስሆን ለአንተ በእርግጥ ምህረትን እለምንልሃለሁ። ማለቱ ብቻ ሲቀር ጌታችን ሆይ በአንተ ላይ ተመካን ወደ አንተም ተመለስን መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው።

✷ የኢስላም መግቢያ በር የሆነው ተውሒድ የሚጠይቃቸው ዋና ዋና ግዴታዎች እነዚያ ናቸው። ይህንን ተውሒድ በእውነት አምኖ፤ ከልቡ ተቀብሎ፤ በአንደበቱ የመሰከረና በተግባር (በሥራ) ያረጋገጠ በአላህ ፈቃድ ጀነት ይገባል። ኃጢአት ሰርቶ ተውባህ ሳያደርግ ቢቀር እንኳ አላህ ሊምረው ወይም የጥፋቱን ያህል በገሀነም ከቀጣው በኋላ ከእሳት አውጥቶ ጀነት ሊያስገባው ይችላል። በነቢያዊ ሀዲስ በተወራው መሠረት ነብዩ ሙሳ አላህን የሚያመልኩበት ልዩ ቃል እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ አላህ «ሙሳ ሆይ ላኢላሀ ኢለሏህ በል» የሚል መልስ ሰጣቸው። እሳቸውም «ጌታዬ ሆይ ይህንንማ ባሮችህ ሁሉ ይሉታል»አሉት። አላህ «ሙሳ ሆይ! ሰባቱ ሰማያትና ሰባቱ ምድር እንዲሁም በውስጣቸው ያለው ነገር በአንድ ሚዛን «ላኢላሀ ኢለሏህ» የሚለው ቃል ደግሞ በሌላ ሚዛን ቢቀመጡ ወይም ቢመዘኑ የላኢላሀ ኢለሏህ ሚዛን ይደፋል ወይም ይመዝናል» አላቸው። ነብያችንም «በጣዕረ ሞት ላይ እያለ የመጨረሻ ንግግሩ ላኢላሀ ኢለሏህ ያለ ጀነት ይገባል» ብለዋል።

እዚህ ላይ ላኢላሀ ኢለሏህ የሚለውን የምስክርነት ቃል በአንደበት ብቻ መናገር በቂ ነውን የሚል ጥያቄ ቢነሳ? መልሱ ከላይ እንዳሰፈርኩት ሁሉ እውነት ሲባል በልብ ሰርፆ በአንደበት የሚነገር፤ በተግባር የሚተረጎም እንጂ በአንደበት መናገር ብቻ በቂ አይለም። ምክንያቱም ቅድመ ሁኔታዎቹን ሊሟሉለት የሚገባ ጉዳይ ነው። እና ከቅድመ ሁኔታዎቹም የተወሰኑት ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. አላህ እውነተኛና አንድ አምላክ መሆኑን፤ ዒባዳ ለእርሱ ብቻ እንጂ ለሌላ ፍጡር የማይፈቀድ፤ ከእርሱ ሌላ ያሉት አማልክት ሁሉ ከንቱ (ባጢል) መሆናቸውን፤ እነዚህ አማልክትም የማይጠቅሙና የማይጎዱ መሆናቸውን ማመን፤
2. ይህንኑ ሀቅ በእርግጠኝነት በማያሻማና በማያወላውል በሌለበት መልኩ በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት፤
3. ይህን ተውሒድ እስከ መጨረሻው አጥብቆ መያዝ፤
4. የአላህን ጌትነትና የሙሐመድን መልዕክተኛነት ወዶ በመቀበል ምስክርነቱ የሚጠይቀውን መስፈርት ሁሉ ተግባራዊ ማድረግ፤
5. የላኢላሀ ኢለሏህን ግዴታዎች ሁሉ መሥራት ለዚሁ ዓላማ ማደርና እውነተኛ ታማኝ መሆን፤
6. በዚህ ረገድ የሚከናወነውን ስራ ሁሉ ለሌላ ዓላማ ሳይሆን ለአላህ ፈቃድ ብቻ ማድረግ፤
7. አላህን መልዕክተኛውን እና ለአላህ ያደሩትንና እርሱን የሚገዙትን ሙዕሚኖች ሁሉ ከልብ መውደድ፤
8. በመጨረሻም አላህ ያዘዘውን ሁሉ መፈጸምና የከለከለውን ነገር ሁሉ መታቀብ፤

ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ አላህን በመፍራትና ምንዳውን ተስፋ በማድረግ፤ ምህረቱን በመከጀል፤ በዚህም የነብያችን ሙሐመድን ተከታይነታችንን በማረጋገጥ ነው። ነብዩ (ﷺ) የነብያት መደምደሚያ ሲሆኑ ይዘውት የመጡት ሸሪዓም ከሳቸው በፊት የተላኩት ነብያት ያመጡትን ህግጋት የሚሽር ነው። ምክንያቱም የርሳቸው ሸሪዓ ከእርሳቸው በፊት የወረዱትን ሸሪዓዎችና ይዘውት የነበረውን ትሩፋት ሁሉ አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ነው። ስለ ዚህ በኢብራሒም ተግባራት በሁሉም ተከተሉ። ለአባቱ ያለው ላይ ሲቀር። በእሱማ አትከተሉት። ምክንያቱም ቀጥሮት እያለ የአላህ ጠላት መሆኑ ሲገለፅለት ከእሱ ንፁህ ሆነ ስለዚህ ለካሃዲያን ምህረትን እንዳትጠይቁ።

رَبَّنَا لَا تَجۡعَلۡنَا فِتۡنَةٗ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ وَٱغۡفِرۡ لَنَا رَبَّنَآۖ إِنَّكَ أَنتَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٥

**5.** ጌታችን ሆይ! ለእነዚያ ለካዱት ሰዎች መሞከሪያ አታድርገን።* ለእኛ ምህረት አድርግልን። ጌታችን ሆይ፣ አንተ አሸናፊና ጥበበኛ ነህ።

✷ ሙጃሒድ ሲናገሩ በእጃችንም ሆነ ከአንተ ዘንድ በሆነ ቅጣት አትቅጣን ምክንያቱም ከሓዲያን በእውነት ላይ በሆኑ ኑሮ ይህ አይደርስባቸውም ነበር በማለት የበለጠ ይጠማሉና ማለት ነው። ከሞካሪዋ (10) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩና በመካ ሰወች መካከል የተካሔደው ከሁደይቢያ ስምምነቶች ነጥቦች መካከል አንዱ ነው፡- ሰልሞ የመጣን ወደ ካፊሮች መመለስ የሚለው ስለነበር ስምምነቱ እንዳበቃ በዚው ቦታ ላይ ሰብዓይሀ ቢንቱል ሀሪስ የተባለች ሴት ሰልማ ስትመጣ ከሀዲው ባሏ በስምምነቱ መሰረት ትመልሰኝ በማለቱ ነው።

لَقَدۡ كَانَ لَكُمۡ فِيهِمۡ أُسۡوَةٌ حَسَنَةٞ لِّمَن كَانَ يَرۡجُواْ ٱللَّهَ وَٱلۡيَوۡمَ ٱلۡأٓخِرَۚ
وَمَن يَتَوَلَّ فَإِنَّ ٱللَّهَ هُوَ ٱلۡغَنِيُّ ٱلۡحَمِيدُ ٦

6. ለናንተ አላህንና የመጨረሻውን ቀን ለሚፈራ ሰው ሁሉ በእነርሱ መልካም አርአያዎች አሉላችሁ። ፊቱን የሚያዞር ሰው ራሱን ብቻ ይጎዳል። አላህ ብቸኛ፤ ተብቃቂና ምስጉን ነውና።

ከሞካሪዋ ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በዚህ ላይ የመጀመሪያው አንቀፅ ሲወርድ ሙስሊሞች በከሃዲ ዘመዶቻቸው ላይ ከፍተኛ ጥላቻ ስላደረገባቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

۞ عَسَى ٱللَّهُ أَن يَجۡعَلَ بَيۡنَكُمۡ وَبَيۡنَ ٱلَّذِينَ عَادَيۡتُم مِّنۡهُم مَّوَدَّةٗۚ
وَٱللَّهُ قَدِيرٞۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ٧

7. አላህ በእናንተና በእነዚያ ከእነርሱ ጋር በተጣላችሁት ሰዎች መካከል መፋቀርን ሊያደርግ ይከጀላል። አላህ ሁሉን ማድረግ ቻይ ነው። አላህ መሀሪና አዛኝ ነውና።

لَّا يَنۡهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ لَمۡ يُقَٰتِلُوكُمۡ فِي ٱلدِّينِ وَلَمۡ يُخۡرِجُوكُم مِّن دِيَٰرِكُمۡ أَن تَبَرُّوهُمۡ
وَتُقۡسِطُوٓاْ إِلَيۡهِمۡۚ إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلۡمُقۡسِطِينَ ٨

8. ለእነዚያ በሃይማኖት ላልተዋጓችሁ ከአገሮቻችሁም ላላወጧችሁ ከሓዲያን መልካም ብትውሉላቸውና ወደ እነርሱ ፍትህ ልትውሉላቸው አላህ አይከለክላችሁም። አላህ ትክክለኞችን (ፍትሃዊያን አማኞች) ይወዳልና።

ከሞካሪዋ ምዕራፍ (8) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የአስማእ ቢንቱ አቡበክር ሲዲቅ እናት ቁተይላህ ለአስማእ ስጦታ ይዛላት መጥታ ነበር። አስማእ ቢንት አቡበክር የእናቷ እምነት ስላልተስተካከለ ስጦታዋን መቀበል መፈቀድ ወይም አለመፈቀዱን ነብዩን (ﷺ) ለመጠየቅ ወደ አይሻ ልዕክት መልክትኛ ልከው ሲጠይቁ ይህን አንቀፅ አነበቡላቸው።

إِنَّمَا يَنۡهَىٰكُمُ ٱللَّهُ عَنِ ٱلَّذِينَ قَٰتَلُوكُمۡ فِي ٱلدِّينِ وَأَخۡرَجُوكُم مِّن دِيَٰرِكُمۡ وَظَٰهَرُواْ عَلَىٰٓ
إِخۡرَاجِكُمۡ أَن تَوَلَّوۡهُمۡۚ وَمَن يَتَوَلَّهُمۡ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلظَّٰلِمُونَ ٩

9. አላህ የሚከለክላችሁ ከእነዚያ በሃይማኖት ሰበብ ከተዋጓችሁና ከቤቶቻችሁም ያወጧችሁ እናንተንም ከሀገር በማውጣት ላይ የረዱትን እንዳትወዳጇቸው ብቻ ነው። እነርሱን ወዳጅ የሚያደርጓቸው ሰዎች ሁሉ እነዚያ እነርሱ ራሳቸዉን በዳዩች ናቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا جَآءَكُمُ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتُ مُهَٰجِرَٰتٖ فَٱمۡتَحِنُوهُنَّۖ ٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِإِيمَٰنِهِنَّۖ
فَإِنۡ عَلِمۡتُمُوهُنَّ مُؤۡمِنَٰتٖ فَلَا تَرۡجِعُوهُنَّ إِلَى ٱلۡكُفَّارِۖ لَا هُنَّ حِلّٞ لَّهُمۡ وَلَا هُمۡ يَحِلُّونَ
لَهُنَّۖ وَءَاتُوهُم مَّآ أَنفَقُواْۚ وَلَا جُنَاحَ عَلَيۡكُمۡ أَن تَنكِحُوهُنَّ إِذَآ ءَاتَيۡتُمُوهُنَّ أُجُورَهُنَّۚ
وَلَا تُمۡسِكُواْ بِعِصَمِ ٱلۡكَوَافِرِ وَسۡـَٔلُواْ مَآ أَنفَقۡتُمۡ وَلۡيَسۡـَٔلُواْ مَآ أَنفَقُواْۚ ذَٰلِكُمۡ حُكۡمُ ٱللَّهِ
يَحۡكُمُ بَيۡنَكُمۡۖ وَٱللَّهُ عَلِيمٌ حَكِيمٞ ١٠

10. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ሴት ምዕመናት ስደተኞች ሆነው ወደ እናንተ በሚመጡበት ጊዜ ለሀይማኖት ብቻ ሲሉ መሰደዳቸውን ፈትኗቸው። አላህ በእምነታቸው ከናንተ ይበልጥ አዋቂ ነው። አማኞችም መሆናቸውን ብታውቁ ወደ ከሓዲያን ባሎቻቸው አትመልሷቸው። እነርሱ ሙስሊም ሴቶች ለከሓዲ ወንዶች አይፈቀዱምና። ከሓዲያን ወንዶችም ለአማኝ ሴቶች የተፈቀዱ አይደሉምና። ያወጡትንም ገንዘብ መህሩን ስጧቸው። መህራቸውንም ከሰጣችኋቸው ብታገቧቸው ኃጢአት የለባችሁም። የከሓዲያንንም ሴቶች የጋብቻ ቃል ኪዳኖች አትያዙ። ሆኖም እናንተ ያወጣችሁትን ገንዘብ ጠይቁ። እነርሱም ያወጡትን ይጠይቁ። ይህ የአላህ ፍርድ ነውና። በመካከላችሁም ይፈርዳል። አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው።

ከሞካሪዋ (10) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በነብዩና በመካ ሰወች መካከል የተካሄደው ከሁደይቢያ ስምምነቶች ነጥቦች መካከል አንዱ፡- ሰልሞ የመጣን ወደ ካፊሮች መመለስ የሚለው ስለነበር ስምምነቱ እንዳበቃ በዚው ቦታ ላይ ሰብዓይህ ቢንቱል ሀሪስ የተባለች ሴት ሰልማ ስትመጣ ከሓዲው ባሏ በስምምነቱ መሰረት ትመልሰኝ በማለቱ ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَإِن فَاتَكُمۡ شَيۡءٞ مِّنۡ أَزۡوَٰجِكُمۡ إِلَى ٱلۡكُفَّارِ فَعَاقَبۡتُمۡ فَـَٔاتُواْ ٱلَّذِينَ ذَهَبَتۡ أَزۡوَٰجُهُم مِّثۡلَ
مَآ أَنفَقُواْۚ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ ٱلَّذِيٓ أَنتُم بِهِۦ مُؤۡمِنُونَ ١١

**11.** ከሚስቶቻችሁም አንዳቸው ወደ ከሓዲያን ቢያመልጧችሁ ቀጥሎም ብትዘምቱባቸው ለእነዚያ ሚስቶቻቸው ለሄዱባቸው ሰዎች ያወጡትን ወጪ ያክል ስጧቸው ያንንም እናንተ በእርሱ ያመናችሁበትን አላህን ፍሩት።

ከሞካሪዋ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከሰለሞች በኋላ እምነቷን ቀይራ አንድ ሰቂፋዊት ባገባቸው ኡሙልሐኪም ቢንት አቡ ሱፍያን ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። በነብዩ (ﷺ) ጊዜ ከሰለሙ ሴቶች መካከል እምነቷን የቀየረች ይህች ሴት ብቻ ናት ይባላል። (ሱዩጢ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِذَا جَآءَكَ ٱلۡمُؤۡمِنَٰتُ يُبَايِعۡنَكَ عَلَىٰٓ أَن لَّا يُشۡرِكۡنَ بِٱللَّهِ شَيۡـًٔا وَلَا يَسۡرِقۡنَ وَلَا يَزۡنِينَ وَلَا يَقۡتُلۡنَ أَوۡلَٰدَهُنَّ وَلَا يَأۡتِينَ بِبُهۡتَٰنٖ يَفۡتَرِينَهُۥ بَيۡنَ أَيۡدِيهِنَّ وَأَرۡجُلِهِنَّ وَلَا يَعۡصِينَكَ فِي مَعۡرُوفٖ فَبَايِعۡهُنَّ وَٱسۡتَغۡفِرۡ لَهُنَّ ٱللَّهَۚ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ١٢

**12.** አንተ ነብይ ሆይ፣ ምዕመናቶቹ በአላህ ምንም ላያጋሩ፣ ላይሰርቁ፣ ላያመነዝሩ፣ ልጆቻቸውን ላይገድሉ፣ በእጆቻቸውና በእግሮቻቸው መካከል የሚቀጣጥፉት ኃጢአትን ላያመጡ (ላይሰሩ)፣ በበጎም ስራ ትዕዛዝን ላይጥሱ ቃል ኪዳን ሊገቡልህ ወደ አንተ በመጡ ጊዜ ቃል ኪዳን ተጋባቸው። ለእነርሱም አላህን ምህረት ለምንላቸው። አላህ በጣም መሀሪና እጅግ በጣም አዛኝ ነውና።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ لَا تَتَوَلَّوۡاْ قَوۡمًا غَضِبَ ٱللَّهُ عَلَيۡهِمۡ قَدۡ يَئِسُواْ مِنَ ٱلۡأٓخِرَةِ كَمَا يَئِسَ ٱلۡكُفَّارُ مِنۡ أَصۡحَٰبِ ٱلۡقُبُورِ ١٣

**13.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ አላህ በእነርሱ ላይ የተቆጣባቸውን ህዝቦች አትወዳጁ። ከሓዲያን ከመቃብር ሰዎች ተስፋ እንደቆረጡ ሁሉ በመጨረሻይቱም ዓለም ምንዳ መኖር በእርግጥ ተስፋ ቆርጠዋል።

ከሞከሪዋ ምዕራፍ (13) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንዳንድ ችግረኛ ሙስሊሞች የሙስሊሞችን ሚስጢር ወደ አይሁዶች በማድረስ ከአይሁዶች አንዳንድ ጥቅማጥቅም ይፈልጉ ስለነበር ከዚህ ትብብራቸው እንዲቆጠቡ ነው (ዋሒዲ።)

ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመርና ዘይድ ኢብኑ ሀሪስ ከተወሰኑ አይሁዶች ጋር በነበራቸው መጠነኛ ፍቅር ምክንያት ነው። (ሱዩጢ) ይህ መልካም አርአያ የሚሆነው ከአላህ ኸይር ለሚመኙ ብቻ ነው። (ይህም የሚሆነው እውነትን ተረድተው ሲሰልሙ ነው። እናም ከመካ መከፈት በኋላ ብዙ ሰዎች ሰልመው ከሙስሊሞች ጋር ፍቅር መስርተዋል። ጂሃድ ተዋግተዋል። አያሌ ኸይሮችንም ፈፅመዋል። ነቢዩ የአቡ ሱፍያንን ልጅ ኡሙ ሐቢባን አግብተዋል። ሆኖም ከእርሱ ጋር ፍቅር የተመሰረተው የፈትሁ መካ ዕለት ከሰለመ ነቢዩን መጥላት ካቆመ በኋላ ነው።

ሙስሊም ሴት ለከሃዲ አትፈቀድምና። ሴት ልጅ በመሰደድ ሳይሆን በመስለሟ ብቻ ከከሃዲ ባሏ ትለያለች።

**ከሞካሪዋ ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-13) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በኢስላም ቀጠሮ ማፍረስና መዋሸት የተከለከለ ነው። ውሸት በሽርክና ኩፍር ውጪ ከወንጀሎች ሁሉ አስከፊ መሆኑን፡
2. በኢስላም ከወንጀል ወደ ወንጀል መሸጋገር አደገኛ ነው። በከፍተኛ ወንጀል ውስጥ የተዘፍቁ ሰዎች ለአላህ ሂዳያ እንደማይታደሉ፤
3. አይሁድ በዒሳ ከማስተባበላቸው በተጨማሪ በነብዩ (ﷺ) በማስተባበል ከፍረዋል። ክርስቲያኖችም ነብዩ (ﷺ) ነብዩ ዒሳን በመካድ ከፍረዋል። በእሳቸው (በዒሳ) የተበሰረላቸውን ነብዩን (ﷺ) አናውቅም በማለት ለኩፍር እንደተዳረጉ፤
4. የነብዩን (ﷺ) ነብይነት ማረጋገጥ፤ አማኞች የታዘዙትን ነገሮች ትክክለኛ ተፈፃሚነት በገሀድ ማየት፤ የነብዩ (ﷺ) ባልደረቦች የተጠየቁትን ድጋፍ እንደሰጡ።
5. ኢስላም የጅሃድን ትልቅነትና የአንድነትን አስፈላጊነት፤ በሀብትና በጉልበት የሚከፈሉ መስዋዕትነቶች የሚሰጣቸው ክብር ምን ያህል ትልቅ እንደሆነ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የሞካሪዋ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (61)
# የሰልፍ ምዕራፍ
(ሱረቱ አስ-ሶፍ)

سُورَةُ الصَّفِّ

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (14) ናቸው።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

سَبَّحَ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلْأَرْضِ ۖ وَهُوَ ٱلْعَزِيزُ ٱلْحَكِيمُ ١

**1.** በሰማያትና በምድር ውስጥ ያሉ ሁሉ አላህን አጠሩ። እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لِمَ تَقُولُونَ مَا لَا تَفْعَلُونَ ٢
كَبُرَ مَقْتًا عِندَ ٱللَّهِ أَن تَقُولُوا۟ مَا لَا تَفْعَلُونَ ٣

**2-3.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፤ የማትሰሩትን ነገር ለምን ትናገራላችሁ? የማትሰሩትን ነገር መናገራችሁ በአላህ ዘንድ በመጠላት እጅግ ከበደ።

ከሰልፍ ምዕራፍ ከ (1-2) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አብደላህ ኢብኑ ሰላም የተባሉ ሰሀብይ ሲናገሩ አንድ ቀን የተወሰኑ ሶሀቦች በአንድ ተቀምጠን ከአላህ ዘንድ ተወዳጅ ስራ ምን እንደሆነ ብናውቅ እንሰራ ነበር በማለታችን ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ብለዋል። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱللَّهَ يُحِبُّ ٱلَّذِينَ يُقَٰتِلُونَ فِي سَبِيلِهِۦ صَفًّا كَأَنَّهُم بُنْيَٰنٌ مَّرْصُوصٌ ٤

**4.** አላህ እነዚያን ልክ እንደተለሰነ ግንብ* የተሰለፉ ሆነው በሃይማኖቱ የሚፋለሙትን ይወዳል።

✴ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒይድ አል ኹድሪ እንዳስተላለፉት አንድ ሰው «በላጩ ሰው ማነው?» ብሎ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጠየቃቸው። እሳቸውም፡- «በአላህ መንገድ ላይ በነፍሱና በገንዘቡ የሚጋደል ነው» አሉ። «ከዚያ በኋላ ማነው?» አላቸው፤ «ከተራራዎቹ መካከል በአንዱ የሚኖርና አላህን የሚገዛ እንዲሁም ሰዎችን ከተንኮል የሚጠብቅ ነው» አሉት።

وَإِذۡ قَالَ مُوسَىٰ لِقَوۡمِهِۦ يَٰقَوۡمِ لِمَ تُؤۡذُونَنِي وَقَد تَّعۡلَمُونَ أَنِّي رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيۡكُمۡۖ
فَلَمَّا زَاغُوٓاْ أَزَاغَ ٱللَّهُ قُلُوبَهُمۡۚ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلۡفَٰسِقِينَ ٥

**5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሙሳም ለህዝቦቹ፦ ህዝቦቼ ሆይ፤ እኔ ወደ እናንተ የአላህ መልዕክተኛ መሆኔን እያወቃችሁ ለምን ታሰቃዩኛላችሁ ባለ ጊዜ የሆነውን አስታውስ። ከእውነት በተዘነበሉ ጊዜ አላህ ልቦቻቸውን አዘነበለባቸው። አላህ አመፀኞችን ህዝቦች አያቀናምና።

وَإِذۡ قَالَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ يَٰبَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ إِنِّي رَسُولُ ٱللَّهِ إِلَيۡكُم مُّصَدِّقٗا لِّمَا بَيۡنَ يَدَيَّ
مِنَ ٱلتَّوۡرَىٰةِ وَمُبَشِّرَۢا بِرَسُولٖ يَأۡتِي مِنۢ بَعۡدِي ٱسۡمُهُۥٓ أَحۡمَدُۖ فَلَمَّا جَآءَهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ قَالُواْ
هَٰذَا سِحۡرٞ مُّبِينٞ ٦

**6.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመርየም ልጅ ዒሳም፦ የኢስራኤል ልጆች ሆይ፤ እኔ ከተውራት በፊት ያለውን የማረጋግጥና ከእኔ በኋላ በሚመጣው መልዕክተኛ ስሙ አህመድ በሆነው የማበስር ስሆን ወደ እናንተ የተላኩ የአላህ መልዕክተኛ ነኝ ባለ ጊዜ የሆነውን አስታውስ። ዒሳ (ሙሐመድ) ግልፅ ታምራቶችን ባመጣላቸው ጊዜ ይህ ግልፅ ድግምት* ነው አሉ።

✷ (ሀ) የአላህ መልዕክተኛም (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ጁበይር ኢብኑ ሙጥዒም እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፦ «እኔ አምስት ስሞች አሉኝ። እነርሱም ሙሐመድ፤ አህመድ፤ ማሒ አላህ (ኩፍርን በእኔ ይደመስሳል)። ሐሽር እኔ (ሰብሳቢ ነኝ በእግሮቼ ላይ የሰው ልጆች የሚሰበሰቡበት)። እኔም ኣተም (መደምደሚያው) ነኝ»

(ለ) የአላህ መልዕክተኛም (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት እንዲህ ብለዋል፦ «ነፍሴ በእጁ በሆነችው በሆነችው በአላህ እምላለሁ የመርየም ልጅ ዒሳ በእርግጥ በመካከላችሁ በፍትህ አስተዳዳሪ ሆኖ የሚወርድበት ጊዜ ተቃርቧል። መስቀልን ይሰባብራል። አሳማዎችን ይገድላል። ጀዝያህን (ግብርን) ያስቀራል። ገንዘብ የሚቀበል ሰው እስከማይገኝ ድረስ ሀብት ይበረክታል»

وَمَنۡ أَظۡلَمُ مِمَّنِ ٱفۡتَرَىٰ عَلَى ٱللَّهِ ٱلۡكَذِبَ وَهُوَ يُدۡعَىٰٓ إِلَى ٱلۡإِسۡلَٰمِۚ
وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ٧

**7.** እርሱ ወደ ኢስላም የሚጠራ ሲሆን በአላህ ላይ ውሸትን ከቀጣጠፈ ሰውም ይበልጥ በደለኛ ማን ነው? አላህ በዳዮችን ህዝቦች አይመራምና።

يُرِيدُونَ لِيُطۡفِـُٔواْ نُورَ ٱللَّهِ بِأَفۡوَٰهِهِمۡ وَٱللَّهُ مُتِمُّ نُورِهِۦ وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡكَٰفِرُونَ ٨

**8.** የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ሊያጠፉ ይሻሉ። አላህ ከሓዲያን ቢጠሉም እንኳ ብርሀኑን ገላጭ ነው።

هُوَ ٱلَّذِيٓ أَرۡسَلَ رَسُولَهُۥ بِٱلۡهُدَىٰ وَدِينِ ٱلۡحَقِّ لِيُظۡهِرَهُۥ عَلَى ٱلدِّينِ كُلِّهِۦ
وَلَوۡ كَرِهَ ٱلۡمُشۡرِكُونَ ٩

**9.** እርሱ (አላህ) ያ አጋሪዎቹ ቢጠሉም መልዕክተኛውን በመምሪያ መጽሐፍና በእውነተኛ ሃይማኖት (በኢስላም) ከሃይማኖቱ ሁሉ በላይ ይፋ ሊያደርገው የላከው ነው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ هَلۡ أَدُلُّكُمۡ عَلَىٰ تِجَٰرَةٖ تُنجِيكُم مِّنۡ عَذَابٍ أَلِيمٖ ١٠ تُؤۡمِنُونَ
بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَتُجَٰهِدُونَ فِي سَبِيلِ ٱللَّهِ بِأَمۡوَٰلِكُمۡ وَأَنفُسِكُمۡۚ ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن
كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ١١ يَغۡفِرۡ لَكُمۡ ذُنُوبَكُمۡ وَيُدۡخِلۡكُمۡ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ
وَمَسَٰكِنَ طَيِّبَةٗ فِي جَنَّٰتِ عَدۡنٖۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ١٢

**10-12.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ከአሳማሚ ቅጣት የሚያድናችሁን ትርፋማ ንግድ ላመላክታችሁን? በላቸው። (እርሱም) በአላህና በመልዕክተኛው ታምናላችሁ። በአላህ መንገድ በገንዘቦቻችሁና በነፍሶቻችሁ ትታገላለችሁ። ይህ ተግባር የምታውቁ ከሆናችሁ ለእናንተ የተሻለ ነው። ኃጢአቶቻችሁን ለእናንተ ይምራል። ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውም ገነቶች ያስገባችኋል። በመኖሪያ ገነቶችም በሚያምሩ ቤቶች ውስጥ ያስቀምጣችኋል። ይህ ታላቅ እድል ነው።

وَأُخۡرَىٰ تُحِبُّونَهَاۖ نَصۡرٞ مِّنَ ٱللَّهِ وَفَتۡحٞ قَرِيبٞۗ وَبَشِّرِ ٱلۡمُؤۡمِنِينَ ١٣

**13.** ሌላይቱንም የምትወዷትን ፀጋ ይሰጣችኋል። እርሷም ከአላህ የሆነ እርዳታና ቅርብ የሆነ አገር መክፈት ነው። ምዕመናንንም አብስር።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ كُونُوٓاْ أَنصَارَ ٱللَّهِ كَمَا قَالَ عِيسَى ٱبۡنُ مَرۡيَمَ لِلۡحَوَارِيِّـۧنَ مَنۡ
أَنصَارِيٓ إِلَى ٱللَّهِۖ قَالَ ٱلۡحَوَارِيُّونَ نَحۡنُ أَنصَارُ ٱللَّهِۖ فَـَٔامَنَت طَّآئِفَةٞ مِّنۢ بَنِيٓ إِسۡرَٰٓءِيلَ
وَكَفَرَت طَّآئِفَةٞۖ فَأَيَّدۡنَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ عَلَىٰ عَدُوِّهِمۡ فَأَصۡبَحُواْ ظَٰهِرِينَ ١٤

**14.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! የመርየም ልጅ ዒሳ ለሐዋሪያቱ:- ወደ አላህ ረዳቴ ማን ነው እንዳለና ሐዋርያቶቹም:- እኛ የአላህ ረዳት ነን እንዳሉት ሁሉ እናንተም የአላህ ረዳቶች ሁኑ፤ ከኢስራኤል ልጆችም አንደኛዋ ጭፍራ አመነች። ሌላይቱም ጭፍራ ካደች። እነዚያን ያመኑትንም በጠላታቸው ላይ አበረታናቸው። ከዚያ እነርሱም አሸናፊዎች ሆኑ።

**ከሰልፍ ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-14) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የዚህ ዓለም ስርዓት ለአላህ ብቸኛ አምላክነትና ሙሉ ምስክር መሆኑን፤
2. ቃልን አለማክበር ከፍተኛ ወንጀል መሆኑን፤
3. የአላህን ዲን ይፋ ለማድረግና ለሰው ልጆች ዘር ለማዳረስ የሚደረገውን ጥረት የሚያደናቅፍን ሁሉ ለማስወገድ እስከ ህይወት መስዋዕትን መክፈል ተገቢ መሆኑን፤
4. ለኢስላም የሚሰሩ አካላት ሁሉ አንድነታቸውን መጠበቅ እንዳለባቸው፤
5. ኢስላም እስከ ዓለም ፍፃሜ ለዓለም ህዝቦች ብቸኛ ሃይማኖት እንዲሆን የተመረጠ መሆኑን፤
6. ነብያት ሁሉ ለህዝቦቻቸው የነብዩን የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) መምጣት እንዳበሰሩ፤
7. በየጊዜው የሚኖሩ ከሓዲያንና ጣኦት አምላኪዎች የሚዋጉት የአላህን ዲን መሆኑን፤
8. ትርፋማው ንግድ ማለት ከአላህ ጋር የሚደረግ ንግድ ብቻ መሆኑን፤
9. በእውነትና በውሸት መካከል በሚደረጉ ትግሎች ሁሉ የመጨረሻው ድል ለትክክለኛ አማኞች ብቻ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የሰልፍ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (62)
# የጁሙዓ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ጁሙዓ)

سُورَةُ الجُمُعَةِ

**የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (11) ናቸው።**
**የሱረቱ አል ጁሙዓ መግቢያ**

የጁምዓ ምእራፍ ከእርም ማድረግ ምእራፍ በኋላ ከመቆጨት ምእራፍ በፊት በ (106) ኛ ተራ ላይ ወረደ። የጁሙዓ ቀን በኢስላም ከቀናት ሁሉ ለየት ያለ ነው። በዚህ የተሰየመው ከዚሁ አንፃር ነው። ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ፀሐይ ከወጣችባቸው ቀናት ሁሉ በላጩ ቀን የጁመዓ ቀን ነው። በርሱ ውስጥ አደም ተፈጥሯል። በርሱም ውስጥ ወደ ጀነት እንዲገባ ተደርጓል። በርሱም ውስጥ ከጀነት እንዲወጣ ተደርጓል።»

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِ ٱلۡمَلِكِ ٱلۡقُدُّوسِ ٱلۡعَزِيزِ ٱلۡحَكِيمِ ١

**1.** በሰማይና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ ንጉስ፤ ቅዱስ፤ (ከጉድለት) (ንፁህ)፤ አሸናፊና ጥበበኛ የሆነውን አላህን ያሞግሳል።

هُوَ ٱلَّذِي بَعَثَ فِي ٱلۡأُمِّيِّـۧنَ رَسُولٗا مِّنۡهُمۡ يَتۡلُواْ عَلَيۡهِمۡ ءَايَٰتِهِۦ وَيُزَكِّيهِمۡ وَيُعَلِّمُهُمُ
ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡحِكۡمَةَ وَإِن كَانُواْ مِن قَبۡلُ لَفِي ضَلَٰلٖ مُّبِينٖ ٢ وَءَاخَرِينَ مِنۡهُمۡ لَمَّا يَلۡحَقُواْ
بِهِمۡۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ٣

**2-3.** እርሱ ያ፣ ለመሃይማን ዐረቦች አንቀፆችን ቁርኣንን በእነርሱ ላይ የሚያነብላቸው፤ የሚያጠራቸውም፤ መጽሐፍንና ጥበብን የሚያስተምራቸውም የሆነን መልዕክተኛ ሙሐመድን ከእነርሱ ውስጥ የላከ ነው። እነርሱም ከእርሱ በፊት በግልፅ ስህተት ውስጥ ነበሩ። ከነሱም ሌሎች ገና ያልተከተሏቸው* በሆኑት ላይ የላከው ነው። እርሱም አሸናፊና ጥበበኛ ነው።

✷ የተከተሏቸው ማለት ሲሆን እነሱም እስከ ዐለም ፍፃሜ ድረስ ኢስላምን የሚቀበሉ ሁሉ ናቸው። ቡኻሪና ሌሎችም ከአቡ ሁረይራህ እንደዘገቡት (በነብዩ አጠገብ ተቀምጠን በነበርንበት ነው ይህ የወረደችው እናም እዚህ ቦታ ሲደርሱ አንድሰው ተነስቶ እኒህ እኛን ያልደረሱብን ያልተከተሉን እነማን ናቸው በማለት ሲጠይቃቸው በሰልማኑል ፋሪሲ ላይ እጃቸውን አስቀምጠው ሂወቴ በእጁ በሆነበት ጌታ ይሁን ብኘ በእምነት ዙሪያ ላይ እንኳን ቢሆን ከእነዚህ የሆኑ ሰዎች ያገኟታል።

ذَٰلِكَ فَضۡلُ ٱللَّهِ يُؤۡتِيهِ مَن يَشَآءُۚ وَٱللَّهُ ذُو ٱلۡفَضۡلِ ٱلۡعَظِيمِ ﴿٤﴾

4. ይህ የአላህ ችሮታ ብቻ ነው። ለሚሻው ሰው ይሰጠዋል። አላህ የታላቅ ችሮታ ባለቤት ነው።

مَثَلُ ٱلَّذِينَ حُمِّلُواْ ٱلتَّوۡرَىٰةَ ثُمَّ لَمۡ يَحۡمِلُوهَا كَمَثَلِ ٱلۡحِمَارِ يَحۡمِلُ أَسۡفَارَۢاۚ بِئۡسَ مَثَلُ ٱلۡقَوۡمِ ٱلَّذِينَ كَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِ ٱللَّهِۚ وَٱللَّهُ لَا يَهۡدِي ٱلۡقَوۡمَ ٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٥﴾

5. የእነዚያ ተውራትን የተጫኑትና ከዚያ ያልተሸከሟት ያልሰሩባት ሰዎች ምሳሌ መጽሐፎችን እንደሚሸከም አህያ ብጤ ነው። የእነዚያ በአላህ አንቀፆች ያስተባበሉት ህዝቦች ምሳሌ ከፋ። አላህ በዳዩችን ህዝቦች አይመራም።*

* ይህ ምሳሌ በተውራት የታዘዙትን ላልፈፀሙ የተሰጠ ምሳሌ ነው። (ስለዚህ እንደእነሱ እንዳትሆኑ። ይህ ምሳሌ ነቢዩ ኹጥባ ላይ እያሉ ወደ ንግዱ ማህበረሰብ የሄዱትን አስመልክቶ የተሰጠ የማስጠንቀቂያ ምሳሌ ነው። ልክ እንደዚሁ በቦታው እያለም ኹጥባ የማያዳማጥ ሁሉ ምሳሌው ነቢዩ እንዳሉት የጁሙዐ ዕለት ኢማሙ እየኸጠበ እያለ የተናገረ ሰው ምሳሌው መፅሐፎችን እንደሚሸከም አህያ ነው። እሱን ዝም በል ያለ ሰው የጁሙዓ ሶላት የለዉም። ይህም የሆነው አይሁዶች ከሰው ሁሉ የተለየ ክብር አለን ብለው ያምኑና ይናገሩ ስለነበር ይህ አባባል ውሼት መሆኑን አስተምራቸው። ፊት ለፊት መገኛኘታችሁ አይቀሬ ነው። (በተለያዩም ስራዎች ላይም ሁናችሁ አላህን አስታውሱ።

قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ هَادُوٓاْ إِن زَعَمۡتُمۡ أَنَّكُمۡ أَوۡلِيَآءُ لِلَّهِ مِن دُونِ ٱلنَّاسِ فَتَمَنَّوُاْ ٱلۡمَوۡتَ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ﴿٦﴾ وَلَا يَتَمَنَّوۡنَهُۥٓ أَبَدَۢا بِمَا قَدَّمَتۡ أَيۡدِيهِمۡۚ وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِٱلظَّٰلِمِينَ ﴿٧﴾ قُلۡ إِنَّ ٱلۡمَوۡتَ ٱلَّذِي تَفِرُّونَ مِنۡهُ فَإِنَّهُۥ مُلَٰقِيكُمۡۖ ثُمَّ تُرَدُّونَ إِلَىٰ عَٰلِمِ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ فَيُنَبِّئُكُم بِمَا كُنتُمۡ تَعۡمَلُونَ ﴿٨﴾

6-8. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እናንተ አይሁዳውያን ሆይ! (የሁዳ የሆናችሁ) ሆይ! ከሰው ሁሉ በተለየ እናንተ ብቻ ለአላህ ወዳጆች ነን ብትሉና በዚያ አባባላችሁ እውነተኞች እንደሆናችሁ እስቲ ሞትን ተመኙ በላቸው። እጆቻቸው ባስቀደሙት ኃጢአት ምክንያት በፍፁም አይመኙትም። አላህ በዳዩችን አዋቂ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያ ከእርሱ የምትሸሹት ሞት እርሱ በእርግጥ አግኛችሁ ነው። ከዚያ ሩቁንና ቅርቡን አዋቂ ወደ ሆነው ጌታ በቂያማ ዕለት ተመላሾች ናችሁ። ትሰሩትም የነበራችሁትን ሁሉ ይነግራችኋል በላቸው።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِذَا نُودِيَ لِلصَّلَوٰةِ مِن يَوۡمِ ٱلۡجُمُعَةِ فَٱسۡعَوۡاْ إِلَىٰ ذِكۡرِ ٱللَّهِ وَذَرُواْ ٱلۡبَيۡعَۚ
ذَٰلِكُمۡ خَيۡرٞ لَّكُمۡ إِن كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ٩ فَإِذَا قُضِيَتِ ٱلصَّلَوٰةُ فَٱنتَشِرُواْ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَٱبۡتَغُواْ
مِن فَضۡلِ ٱللَّهِ وَٱذۡكُرُواْ ٱللَّهَ كَثِيرٗا لَّعَلَّكُمۡ تُفۡلِحُونَ ١٠ وَإِذَا رَأَوۡاْ تِجَٰرَةً أَوۡ لَهۡوًا ٱنفَضُّوٓاْ
إِلَيۡهَا وَتَرَكُوكَ قَآئِمٗاۚ قُلۡ مَا عِندَ ٱللَّهِ خَيۡرٞ مِّنَ ٱللَّهۡوِ وَمِنَ ٱلتِّجَٰرَةِۚ وَٱللَّهُ خَيۡرُ ٱلرَّٰزِقِينَ ١١

**9-11.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! በአርብ (በጁሙዓ) ቀን ለስግደት ጥሪ በተደረገ ጊዜ ወደ አላህ ማውሳት (ኹጥባ ሶላት) ሂዱ። መሸጥንም ተው። ይህ የምታውቁ ብትሆኑ ለእናንተ በጣም የተሻለ ነው። ሶላቷ በተፈፀመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑና የአላህን ችሮታ ፈልጉ። ልትድኑ ይከጀላልና አላህንም በብዙው አውሱ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ንግድን ወይም ዛዛታን ባዩ ጊዜም ቆመህ የተውህ ሲሆኑ ወደ እርሷ ይበተናሉ። ከአላህ ዘንድ ያለው ከዛዛታም ከንግድም በላጭ ነው። አላህ ከሰጭዎች ሁሉ ይበልጥ ሲሳይን ሰጪ ነው በላቸው።

ከጁመዓ ምዕራፍ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- (ሀ) አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ (ግመሌን አስሬ በአላህ ልመካ ወይስ ልልቀቃትና በአላህ ልመካ ሲላቸው ነብዩ (ﷺ) እሰራትና በአላህ ተመካ አሉት። ቲርሚዚ። ከላይ የተጠቀሰው አንቀፅና የነብዩ ሀዲስ የሚያሳዩት ሰዎች በአላህ መመካት ግዴታቸው ቢሆንም ራሳቸውን ለመቻል እንቅስቃሴ ማድረግ ከተወኩል ጋር ፈፅሞ አይቃረንም የሚለውን መልዕክት ያስተምራሉ። ነብያት ተቀጥረው ይሰሩት እንደነበር ነብዩ (ﷺ) አቡበክር እና ዑመርም ተቀጥረው ሰርተዋል። እንዲያውም ኢስላም ሁለቱንም አጣምሮ መያዝን ነው አበክሮ የሚመክረው አንድ ቀን ከየመን የመጡ ሰዎች ዑመር ኢብኑልኸጣብ እነማን ናቸው ብለው ጠይቀው በአላህ ተመኪዎች ነን ስላሏቸው እናንተ ሰነፎች ናችሁ። በአላህ ተመኪ ማለት ዘርን በምድር ላይ አሳርፎ በአላህ የሚመካ ነው አሏቸው።

(ለ) የመዲና ሰዎች ከፍተኛ ረሀብና ድርቅ ስላጋጠማቸው ነብዩ (ﷺ) በኹጥባ ላይ እያሉ የንግድ ግመሎች ወደ መዲና ከተማ ሲደርሱ። አስራ ሁለት ወንዶች ሰባት ሴቶች ብቻ ኹጥባ እያዳመጡ ሲቀሩ ሁሉም ጥለዋቸው በመሄዳቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

### ከጁምዓ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-11) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. የጁምዓ ሶላት በሁሉም ሙስሊሞች ላይ ግዴታ ነው። የጁምዓ አዛን በተሰማ ጊዜ ለሶላት ከሚደረግ ዝግጅት በስተቀር ሌላውን ነገር ሁሉ መሸጥም መቆፈርም... መተው ይገባል። የጁምዓ ቀን ኹጥባዎች ግዴታ መሆናቸውና በሰዓቱ ተገኝቶ ማድመጡ አስፈላጊ ነው። ኢማሙ ኹጥባ ላይ እያለ የተናገረ ሰው ምሳሌው «መፅሐፎችን እንደሚሸከም አህያ ነው» ብለዋል።

   ኹጥባን ማዳመጡ ክብደቱ በዚህ አይወሰንም በኹጥባ ወቅት የተናገረ ሰው ዝም በሉ ያለ ሰው የጁምዓ ሶላት የለውም ብለዋል።

2. ነብዩ የስራን አስፈላጊነት በተመለከተ ሰዎች በአላህ ብቻ ተመክተው እጃቸውን አጣጥፈው መቀመጥ እንደሌለባቸው፤ በሁሉም ሙስሊም ላይ ግዴታ የሆነችውን የጁምዓ ሶላትን እንኳን አስመልክቶ አላህ በቁርአኑ እንዲህ ብሏል «... ሶላቲቱም በተፈፀመች ጊዜ በምድር ላይ ....።» ይህ የሰው ልጆች በምድር ላይ ቆይታችሁ አላህን ከመገዛት ጎን ለጎን መስራት የአላህ ትሩፋት መፈለግም እንዳለባቸው ያሳያል።
3. በዱንያ ላይ አንድ ሙስሊም አላህን ተወኩል አድርጎ በስራ ፈትነት መቀመጥ እንደሌለበት ሁሉ የዱንያ ስራዎችን በአኼራ ስራው ማስበለጥም አይኖርበትም። ምክንያቱም የአኼራ ስራ ከሁሉም ይበልጣልና ነው።
4. ማንኛውም ሙስሊም መጥፎ ነገር ትዝ ሲለው አላህ ዘንድ ያለውን ትልቅ ምንዳ ማስታወስ አለበት።
5. በዘረ ጥሩነት መመካት አይቻልም።
6. በተማረው ሰላማዊ እውቀት የማይጠቀም የተጫነችውን እንደማትበላ አህያ የሚመስል መሆኑን፤ አላህ በቁርአን እንዲህ አለ፦ የእነዚህ ተውራትን የተጫኑትና ከዚያም ያልተሸከሟት (ያልሰሩባት) ሰዎች ምሳሌ መፅሐፎችን እንደሚሸከም አህያ ቢጤ ነው። የእነዚያ በአላህ አናቅፅ ያስተባበሉ ህዝቦች ምሳሌ ከፋ!

## በአላህ ፈቃድ የጁሙዓ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (63)
## የመናፍቃን ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ሙናፊቁን)

سُورَةُ المُنَافِقُونَ

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (11) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِذَا جَآءَكَ ٱلۡمُنَٰفِقُونَ قَالُواْ نَشۡهَدُ إِنَّكَ لَرَسُولُ ٱللَّهِۗ وَٱللَّهُ يَعۡلَمُ إِنَّكَ لَرَسُولُهُۥ
وَٱللَّهُ يَشۡهَدُ إِنَّ ٱلۡمُنَٰفِقِينَ لَكَٰذِبُونَ ١

**1.** መናፍቃን በመጡህ (ወደ አንተ በመጡ) ጊዜ አንተን የአላህ መልዕክተኛ መሆንህን በእርግጥ (ምለን) እንመሰክራለን ይላሉ። አላህም አንተ በእርግጥ መልዕክተኛው መሆንህን ያውቃል። አላህም መናፍቃንን ውሸታሞች መሆናቸውን ይመሰክራል።

ٱتَّخَذُوٓاْ أَيۡمَٰنَهُمۡ جُنَّةً فَصَدُّواْ عَن سَبِيلِ ٱللَّهِۚ إِنَّهُمۡ سَآءَ مَا كَانُواْ يَعۡمَلُونَ ٢
ذَٰلِكَ بِأَنَّهُمۡ ءَامَنُواْ ثُمَّ كَفَرُواْ فَطُبِعَ عَلَىٰ قُلُوبِهِمۡ فَهُمۡ لَا يَفۡقَهُونَ ٣

**2-3.** መሐላዎቻቸውን ጋሻ አድርገው ያዙ። ከአላህም መንገድ ከለከሉ። እነርሱ ይሰሩት የነበሩት ነገር ሁሉ ከፋ። ይህ እነርሱ (በምላስ)፤ ያመኑ ከዚያ በልብ የካዱ በመሆናቸው ነው። በልቦቻቸውም ላይ ታተመባቸው። ስለዚህ እነርሱ አያውቁም።

۞ وَإِذَا رَأَيۡتَهُمۡ تُعۡجِبُكَ أَجۡسَامُهُمۡۖ وَإِن يَقُولُواْ تَسۡمَعۡ لِقَوۡلِهِمۡۖ كَأَنَّهُمۡ خُشُبٞ مُّسَنَّدَةٞۖ
يَحۡسَبُونَ كُلَّ صَيۡحَةٍ عَلَيۡهِمۡۚ هُمُ ٱلۡعَدُوُّ فَٱحۡذَرۡهُمۡۚ قَٰتَلَهُمُ ٱللَّهُۖ أَنَّىٰ يُؤۡفَكُونَ ٤

**4.** ባየሃቸውም ጊዜ አካሎቻቸው ያስደንቁሃል። ቢናገሩም ንግግራቸውን ታዳምጣለህ። እነርሱ ልክ ወደ ግድግዳ የተጠጉ ግንዶችን ይመስላሉ። ጩኸትን ሁሉ በእነርሱ ላይ ነው ብለው ያስባሉ። እነርሱ ጣላቶች ናቸውና ተጠንቀቃቸው። አላህ ይጋደላቸው። (ከእምነት) እንዴት ይመለሳሉ (ያፈገፍጋሉ)።

وَإِذَا قِيلَ لَهُمْ تَعَالَوْا۟ يَسْتَغْفِرْ لَكُمْ رَسُولُ ٱللَّهِ لَوَّوْا۟ رُءُوسَهُمْ وَرَأَيْتَهُمْ يَصُدُّونَ وَهُم
مُّسْتَكْبِرُونَ ﴿٥﴾ سَوَآءٌ عَلَيْهِمْ أَسْتَغْفَرْتَ لَهُمْ أَمْ لَمْ تَسْتَغْفِرْ لَهُمْ لَن يَغْفِرَ ٱللَّهُ لَهُمْ ۚ إِنَّ
ٱللَّهَ لَا يَهْدِى ٱلْقَوْمَ ٱلْفَٰسِقِينَ ﴿٦﴾

5-6. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)) ለእነርሱም፡- ኑ የአላህ መልዕክተኛ ለእናንተ ምህረትን ይለምንላችኋል በተባሉ ጊዜ በማፌዝ ራሶቻቸውን ያዞራሉ። እነርሱም ትዕቢተኞች ሆነው ሲሸሹ ታያቸዋለህ። ምህረትን ብትለምንላቸው ባትለምንላቸውም በእነርሱ ላይ ሁሉም እኩል ነው። አላህ ለእነርሱ በፍፁም አይምርም። አላህ አመፀኛ ህዝቦችን አይመራምና።

ከመናፍቃን (5) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አብደላህ ቢን ኡበይ ወደ ነብዩ (ﷺ) ሂደህ አላህን ምህረት ቢጠይቁልህ ተብሎ ሲመከር አንገቱን እያወዛወዘ በማፌዙ ነው። (ሱዩጢ)

ከመናፍቃን (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ከእሱረቱ አት. ተውባ (80) ኛ ቁጥር ላይ ያለው አንቀፅ ሲወርድና ነብዩ (ﷺ) ጉዳዩ እንደዚህ ቢሆንም ከሰባ በላይ እጨምርለታለሁ በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደና ቢጨምርለትም ምንም ጥቅም እንደሌለው የገለፀላቸው። ሱዩጢ።

هُمُ ٱلَّذِينَ يَقُولُونَ لَا تُنفِقُوا۟ عَلَىٰ مَنْ عِندَ رَسُولِ ٱللَّهِ حَتَّىٰ يَنفَضُّوا۟ ۗ وَلِلَّهِ خَزَآئِنُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلْأَرْضِ وَلَٰكِنَّ ٱلْمُنَٰفِقِينَ لَا يَفْقَهُونَ ﴿٧﴾

7. እነርሱ፡- እነዚያ ከአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ያሉት ሰዎች እስከሚበታተኑ ድረስ ምፅዋት አትስጡ የሚሉ ናቸው። የሰማያትና የምድር ድልቦች የአላህ ብቻ ናቸው። ግን መናፍቃን አያውቁም።

يَقُولُونَ لَئِن رَّجَعْنَآ إِلَى ٱلْمَدِينَةِ لَيُخْرِجَنَّ ٱلْأَعَزُّ مِنْهَا ٱلْأَذَلَّ ۚ وَلِلَّهِ ٱلْعِزَّةُ وَلِرَسُولِهِۦ
وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَلَٰكِنَّ ٱلْمُنَٰفِقِينَ لَا يَعْلَمُونَ ﴿٨﴾

8. ወደ መዲና ብንመለስ አሸናፊው ወራዳውን በእርግጥ ከእርሷ ያስወጣል ይላሉ። አሸናፊነትም ለአላህ ለመልዕክተኛው እና ለምዕምና ብቻ ነው። ግን መናፍቃን አያውቁም።

ከመናፍቃን ከ (7-8) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ዘይድ ኢብኑ አርቀም እንዳሉት ከአስመሳዮች የተወሰኑ አብረውን በነበሩት ዘመቻ ላይ ሳለን አብደላህ ቢን ዑበይ የሚባል የአስመሳዮች አለቃ ወደ መዲና ስንመለስ ክብር ያለው ክብረ ቢስን ለሀገሩ ያስወጣል ብሎ ሲናገር ስለሰማሁ ወዲውያኑ ለነብዩ ሂጄ ነገርኳቸው ኢብኑ ዑበይ ግን አስጠርተው ሲጠይቁት ወላሂ አላልኩም በማለቱ በዚህ ጊዜ ዘመዶቼ ምን አስፈለገህ እና ነው ወደ እዚህ ችግር የገባኸው

በማለት ናቁኝ እኔም ተመልሼ በሁኔታው አዝኜ እንቅልፍ አልወስድ ብሎኝ በመበሳጨት ላይ እያለሁ ጠዋቱኑ ነብዩ (ﷺ) አሰጠሩኝ እና ፈገግ በማለት ደስ ይበልህ አላህ ምክንያትህን አውርዶልሃል እውነተኛነትህን አረጋግጦልሃል ብለዋል።

يَـٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ لَا تُلْهِكُمْ أَمْوَٰلُكُمْ وَلَآ أَوْلَـٰدُكُمْ عَن ذِكْرِ ٱللَّهِ ۚ
وَمَن يَفْعَلْ ذَٰلِكَ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ هُمُ ٱلْخَـٰسِرُونَ ﴿٩﴾

**9.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ አላህን ከማስታወስ አያታልሏችሁ (አያዘናጓዋችሁ)። ይህንንም የሚሰሩ ሰዎች እነዚያ እነርሱ ከሳሪዎች ናቸው።

وَأَنفِقُوا۟ مِن مَّا رَزَقْنَـٰكُم مِّن قَبْلِ أَن يَأْتِىَ أَحَدَكُمُ ٱلْمَوْتُ فَيَقُولَ رَبِّ لَوْلَآ أَخَّرْتَنِىٓ إِلَىٰٓ
أَجَلٍ قَرِيبٍ فَأَصَّدَّقَ وَأَكُن مِّنَ ٱلصَّـٰلِحِينَ ﴿١٠﴾ وَلَن يُؤَخِّرَ ٱللَّهُ نَفْسًا إِذَا جَآءَ أَجَلُهَا ۚ
وَٱللَّهُ خَبِيرٌۢ بِمَا تَعْمَلُونَ ﴿١١﴾

**10-11.** አንዳችሁንም ሞት ሳይመጣበትና ጌታየ ሆይ፣ እንድመፀውተውና በደጋጎችም ሰዎች እንድሆን ጥቂት ጊዜ ብታቆየኝ ኖሮ እምኛለሁ ከማለቱ በፊት ከሰጠናችሁ ሲሳይ✶[1] ለግሱ። ማንኛይቱም ነፍስ✶[2] የሞት ጊዜዋ በመጣባት ጊዜ አላህ በፍፁም አያቆያትም። አላህም በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው።

✶1 ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «በየቀኑ ሁለት መላዕክቶች ከሰማይ ይወርዳሉ ከዚያም «አላህ ሆይ! የሚሰጥን ሰው ምትክ ስጠው። ሌላኛው ደግሞ «አላህ ሆይ! ማንኛውንም የማይሰጥን ሰው ጥፋት ስጠው (አጥፋበት ይላሉ)።»

✶2 ከመናፍቃን ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-11) ያሉት አናቅፅ ጥቅል መልዕክት፦

1. የመናፍቃንን ባህሪያት መጥፎ ተግባር መዘርዘር፤
2. ነብዩን ለማጥቃት ያሴሩትን መናፍቃን ማጋለጥ፤
3. አማኞች በመናፍቃን መመሳሰል እንደሌለባቸው ማስጠንቀቅ፤

**ከመናፍቃን ከአንቀፅ (1-11) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፦**

1. መናፍቃን በኢስላም ላይ ያላቸው አደጋ ከከሓዲያን፣ ከጣኦት አምላኪዎች ከአይሁድ የባሱ መሆኑን፤
2. የኢስላም አስተምህሮት በመዲና በጀመረበት ጊዜ የነበሩት ጠላቶቹ ብዛት፤
3. ቁርአን አስመሳዮች በውስጣቸው ያሰቡትን በማጋለጥ ሴራቸውን በማፍረስ ዘላለማዊ ተዐምርነቱን ማረጋገጥ፤
4. ከመናፍቃን ግልፅ ባህሪያቶች መካከል ውሸት፤ መሀላ ማብዛት፤ ፍርሃት፤ ለሀገርም ሆነ ለወገን ጥቅም አለማበርከት፤ ቀጠሮ ማፍረስ፤ ቃል አለመጠበቅ፤ ሲከራከሩ መዋሸት እና ኩራት መሆናቸውን፤

5. መናፍቃን ኢስላምን ለማጥፋት የሚችሉት ዘዴ ሁሉ እንደሚጠቀሙ፤
6. በመናፍቃ ላይ ጦርነት ያልታወጀበት ዋናው ምክንያት ላይ ላዩን ሙስሊም ነን ይሉ ስለነበር መሆኑን፤
7. አማኝ ነኝ ባይ ሁሉ የሞት ቀን ደርሶ ሙቶ ከመፀፀቱ በፊት ጊዜውን በሙሉ በመልካም ስራ ላይ ማሳለፍ እንዳለበት፤
8. አላህ መናፍቃንን፤ ከሓዲያንን እና አጋሪዎችን እንደማይምር እና በዚሁ እምነታቸው ላይ ከሞቱ ለእነሱ የሚደረገው ፀሎት ምንም ፋይዳ እንደሌለው፤
9. ትክክለኛው ክብር ለምእመናን ብቻ መሆኑን፤
10. ኩራት የከሓዲያን መገለጫ ባህሪ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የመናፍቃን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (64)
## የመቆጬት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አት-ተጋቡን)

سُورَةُ التَّغَابُنِ

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (18) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

يُسَبِّحُ لِلَّهِ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَمَا فِي ٱلۡأَرۡضِۖ لَهُ ٱلۡمُلۡكُ وَلَهُ ٱلۡحَمۡدُۖ
وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ١

1. በሰማያት ውስጥም ሆነ በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ አላህን ያ ሞግሳል። ንግስናው የእርሱ ብቻ ነው። ምስጋናም ለእርሱ ብቻ ነው። እርሱም በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነው።

هُوَ ٱلَّذِي خَلَقَكُمۡ فَمِنكُمۡ كَافِرٞ وَمِنكُم مُّؤۡمِنٞۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ بَصِيرٌ ٢

2. እርሱ ያ የፈጠራችሁ ነው። ከእናንተም መካከል ከሓዲ አለ። ከእናንተም መካከል አማኝ አለ። አላህ የምትሰሩትን ሁሉ ተመልካች ነው።

خَلَقَ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضَ بِٱلۡحَقِّ وَصَوَّرَكُمۡ فَأَحۡسَنَ صُوَرَكُمۡۖ وَإِلَيۡهِ ٱلۡمَصِيرُ ٣

3. (እርሱ) ሰማያትንና ምድርን በእውነት ፈጠረ። ቀረፃችሁም። ከዚያ ቅረፃችሁን አሳመረ። መመለሻችሁም ወደ እርሱ ብቻ ነው።

يَعۡلَمُ مَا فِي ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلۡأَرۡضِ وَيَعۡلَمُ مَا تُسِرُّونَ وَمَا تُعۡلِنُونَۚ
وَٱللَّهُ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ٤

4. በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለውን ሁሉ ያውቃል። የምትደብቁትንም ሆነ የምትገልጡትን ያውቃል። አላህም በልቦቻቸው ውስጥ ያለውን ሁሉ አዋቂ ነውና።

أَلَمۡ يَأۡتِكُمۡ نَبَؤُاْ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِن قَبۡلُ فَذَاقُواْ وَبَالَ أَمۡرِهِمۡ وَلَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ ٥ ذَٰلِكَ بِأَنَّهُۥ كَانَت تَّأۡتِيهِمۡ رُسُلُهُم بِٱلۡبَيِّنَٰتِ فَقَالُوٓاْ أَبَشَرٞ يَهۡدُونَنَا فَكَفَرُواْ وَتَوَلَّواْۚ وَّٱسۡتَغۡنَى ٱللَّهُۚ وَٱللَّهُ غَنِيٌّ حَمِيدٞ ٦

**5-6.** የእነዚያ ከአሁን በፊት የካዱትና የክህደታቸውን ቅጣት የቀመሱ ህዝቦች ወሬ አልመጣላችሁምን? ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣት አለባቸው። ይህ (ቅጣት) እርሱ መልዕክተኞቻቸው አአስረጂዎችን ይዘው ሲመጡላቸው ሰዎች ይመሩናልን? ስላሉና ስለ ካዱ፤ ከእምነትም ስለ ዞሩ ነው። አላህ ከእነርሱ እምነት ተብቃቃ። አላህ ተብቃቂና ምስጉን ነውና።

زَعَمَ ٱلَّذِينَ كَفَرُوٓاْ أَن لَّن يُبۡعَثُواْۚ قُلۡ بَلَىٰ وَرَبِّي لَتُبۡعَثُنَّ ثُمَّ لَتُنَبَّؤُنَّ بِمَا عَمِلۡتُمۡۚ وَذَٰلِكَ عَلَى ٱللَّهِ يَسِيرٞ ٧ فَـَٔامِنُواْ بِٱللَّهِ وَرَسُولِهِۦ وَٱلنُّورِ ٱلَّذِيٓ أَنزَلۡنَاۚ وَٱللَّهُ بِمَا تَعۡمَلُونَ خَبِيرٞ ٨

**7-8.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች በፍፁም የማይቀሰቀሱ መሰላቸው። አይደለም በጌታየ ይሁንብኝ ትቀሰቀሳላችሁ። ከዚያ ትፈፅሙት የነበረውን ተግባራችሁን ትናገራላችሁ። ይህ ተግባር ለአላህ ቀላል ነው በላቸው። በአላህ በመልዕክተኛውና በዚያም ባወረድነው ብርሃን እመኑም። አላህ ምየምትሰሩትን ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነውና።

يَوۡمَ يَجۡمَعُكُمۡ لِيَوۡمِ ٱلۡجَمۡعِۖ ذَٰلِكَ يَوۡمُ ٱلتَّغَابُنِۗ وَمَن يُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ وَيَعۡمَلۡ صَٰلِحٗا يُكَفِّرۡ عَنۡهُ سَيِّـَٔاتِهِۦ وَيُدۡخِلۡهُ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۚ ذَٰلِكَ ٱلۡفَوۡزُ ٱلۡعَظِيمُ ٩

**9.** (ይኸውም) ለመሰብሰቢያው ቀን የሚሰበስባችሁ እለት (አስታውሱ)። ይህ ቀን የቁጭት ቀን ነው። በአላህ የሚያምንና መልካም ተግባር የፈፀመ ሰው ወንጀሉን ያብስለታል። ከስሮቿ ወንዞች የሚፈሱባት ጀነትም ለዘላለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ ያስገባዋል። ይህ ታላቅ እደለኝነት ነው።

وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَآ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلنَّارِ خَٰلِدِينَ فِيهَاۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ١٠

**10.** እነዚያም በአላህ የካዱትና በተአምሮቻችን ያስተባበሉ የዝንታለም በውስጡ ዘውታሪዎች ሲሆኑ የእሳት ባለቤቶች ማለት እነርሱ ናቸው። (ጀሀነም) መመለሻነቷ ምን ይከፋ!

مَآ أَصَابَ مِن مُّصِيبَةٍ إِلَّا بِإِذۡنِ ٱللَّهِۗ وَمَن يُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ يَهۡدِ قَلۡبَهُۥۚ
وَٱللَّهُ بِكُلِّ شَيۡءٍ عَلِيمٞ ١١

**11.** ከመከራም በአላህ ፈቃድ ቢሆን እንጂ ማንንም አይነካም። በአላህ የሚያምን ሰው አላህ ልቡን ለትግስት ይመራዋል። አላህ በሁሉም ነገር አዋቂ ነው።

وَأَطِيعُواْ ٱللَّهَ وَأَطِيعُواْ ٱلرَّسُولَۚ فَإِن تَوَلَّيۡتُمۡ فَإِنَّمَا عَلَىٰ رَسُولِنَا ٱلۡبَلَٰغُ ٱلۡمُبِينُ ١٢
ٱللَّهُ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَۚ وَعَلَى ٱللَّهِ فَلۡيَتَوَكَّلِ ٱلۡمُؤۡمِنُونَ ١٣

**12-13.** አላህን ተገዙ መልዕክተኛውንም ታዘዙ። ብትዞሩም መልዕክተኛውን አትጎዱም። በመልዕክተኛችንም ላይ ያለበት በግልፅ ማድረስ ብቻ ነው። አላህ ከእርሱ በስተቀር አምላክ የለም። አማኞች በአላህ ይመኩ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِنَّ مِنۡ أَزۡوَٰجِكُمۡ وَأَوۡلَٰدِكُمۡ عَدُوّٗا لَّكُمۡ فَٱحۡذَرُوهُمۡۚ
وَإِن تَعۡفُواْ وَتَصۡفَحُواْ وَتَغۡفِرُواْ فَإِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٞ رَّحِيمٌ ١٤

**14.** እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከሚስቶቻችሁና ከልጆቻችሁ ከአላህ መንገድ በማስተጓጎል ለእናንተ ጠላቶች የሆኑ አሉ። ስለዚህ ተጠንቀቋቸው። ይቅርታ ብታደርጉ፤ ብታልፏቸውም፤ ብትምሩዋቸውም፤ አላህ በጣም መሀሪ፤ አዛኝ ነው።

إِنَّمَآ أَمۡوَٰلُكُمۡ وَأَوۡلَٰدُكُمۡ فِتۡنَةٞۚ وَٱللَّهُ عِندَهُۥٓ أَجۡرٌ عَظِيمٞ ١٥

**15.** ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁ ለእናንተ መፈተኛ ብቻ ናቸው። አላህም ከእርሱ ዘንድ ታላቅ ምንዳ አለ።

فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ مَا ٱسۡتَطَعۡتُمۡ وَٱسۡمَعُواْ وَأَطِيعُواْ وَأَنفِقُواْ خَيۡرٗا لِّأَنفُسِكُمۡۗ
وَمَن يُوقَ شُحَّ نَفۡسِهِۦ فَأُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلۡمُفۡلِحُونَ ١٦

**16.** አላህንም የቻላችሁትን ያህል ፍሩት*። ትዕዛዙን ስሙም፤ ታዘዙም፤ ለግሱም፤ ለነፍሶቻችሁ መልካምን ይሰጣችኋልና። የነፍሶቻቸዉን ንፍገት የሚጠበቁ ሰዎች ሁሉ እነዚያ እነርሱ ፍላጎታቸውን የሚያገኙ ናቸው።

ከመቆጨት ምዕራፍ (16) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በዒምራን ቤተ ሰቦች ላይ በ (102) ኛው አንቀፅ አላህን በሚገባው ልክ ፍሩት የሚለው የቁርኣን አንቀፅ ሲወርድ ሰዎች በዒባዳ ላይ ሲቆሙ እግራቸው እስከሚያብጥ፤ ግንባራቸው እስከሚቆስል ትዕዛዙን ለመተግበር ቢሞክሩም ሁኔታው አሳስቧቸው እያሉ ከአቅማቸው በላይ እንደማይገደዱ ለማሳወቅ ይህ አንቀፅ ወረደ። (ሱዩጢ)

✷ አንቀፁ ብዙ ጊዜ ምሁራን ለብዙ ችግሮች መፍቲሄ ይሆን ዘንድ በየ አጋጣሚው የሚያወሱት አንቀፅ ነው። ምክንያቱም አላህን መፍራት የሚቻለው በአቅም ልክ በመሆኑ ነው። ስለሆነም ይህ አንቀፅያንን አንቀፅ ይሺረዋል ማለት ነው።

በመሆኑም ማንም ሰው ከአቅሙ በላይ የሆነ ነገር መስራት አይገደደም። ከፊሉን ችሎ ከፊሉን ባይችል የቻለዉን ብቻ ነው መስራት የሚገደደው። ለምሳሌ ያክል ከዚህ ያሉትን ነገሮች እንመልከት:

1. ቡኻሪና ሙስሊም ከአቡ ሁረይራ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ«...አንድን ነገር እንድትሰሩ ሳዝዛችሁ የቻላችሁትን ፈፅሙ። ....» ብለዋል።
2. ጥቀምና ጉዳት ያለው ነገር ከተከሰተ ጉዳቱን ተጠንቅቆ ጥቅሙን ማግኜት ከተቻለ ጥሩ ነው ካልሆነ ግን እንደሁኔታው ጉዳቱን መከላከል ይገባል።
3. ለሶላት ዉዱእ ማድረግ ግዴታ ነው፤ ነገርግን ዉሃን መጠቀም ካልተቻለ ወደ ተየሙም ይከዳል።
4. ፈረድ ሶላት ቁሞ መስገድ ግዴታ ነው፤ ካልታቻለ ግን ተቀምጦም ይሰገዳል። የዒምራን ኢብኑ ሀሰይን ሐዲስ እዚህ ላይ ይጠቀሳል። «....»
5. ረመዷንን መፆም ለቻለ ግዴታው ነው። ካልቻል ፊዳ ይከፍላል።
6. ሐጅም ሲችል ብቻ ነው የሚገደደው። በእነዚህ እና በሌሎችም ጉዳዮች ላይ ይጠቀሳል።

ከመቆጨት ምዕራፍ (14) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- በመካ አንዳንድ ሰዎች በሰለሙ ጊዜ ወይም ሰልሞ ሊሰደድ ሲል ቤተሰቦቹ ማለትም ሚስቱ ልጆቹ ያስቸግሩትና ያሳስቡት እንዲሁም እየወቀሱ ከስደት ያሳንፉት ስለነበርና ሙስሊም የሆነ ሰው የቤተሰብ ፍቅር ከአላህ ዲን እንዳያዘናጋው ለማስጠንቀቅ ነው። (ዋሒዲ እና ሲዩጢ)

إِن تُقۡرِضُواْ ٱللَّهَ قَرۡضًا حَسَنٗا يُضَٰعِفۡهُ لَكُمۡ وَيَغۡفِرۡ لَكُمۡۚ وَٱللَّهُ شَكُورٌ حَلِيمٌ ﴿١٧﴾
عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ وَٱلشَّهَٰدَةِ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡحَكِيمُ ﴿١٨﴾

**17-18.** ለአላህ መልካም ብድርን ብታበድሩት (ምንዳውን) ለእናንተ ይደራርበዋል። ለእናንተም ይምራል። አላህ አመስጋኝና ታጋሽ ነውና። ስውሩንም ይፋውንም አዋቂ ኃያል፤ ጥበበኛ ነው።

**ከመቆጨት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-18) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:-**

1. አላህ በምሉዕ ባህሪያት ሁሉ የሚገለፅ ከጎደሎ ባህሪያ ሁሉ የፀዳ ዓለም በሙሉ እሱን የሚያሞግሰው ይህም ለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ለኃያልነቱ ለሙሉ ችሎታው ማረጋገጫ መሆኑን፤
2. የሰው ልጅ በዚህ ዓለም ካሉት ፍጡሮች ሁሉ ያማረ መሆኑንና አላህ በመልካም ቅርፅ የቀረፀው ከፍጡሮች ሁሉ ምርጥ ያደረው በሰማይና በምድር ውስጥ ያሉትን ሁሉ ለሱ አገልግሎት እንዲሰጡ ያደረገለት በመሆኑ ጌታውን ማመስገን፤ በብቸኝነት ማምለክ እንዳለበት፤
3. ከሓዲያንና ጣኦት አምላኪያን ያለምንም መረጃ ከሞት በኋላ መነሳት የለም እንደሚሉ፤

4. ታላቁ ቁርኣን ብርሃን ቢሆንም አላህ የፈለገውን ሰው ብቻ በሱ ወደ ቀናው መንገድ የሚመራ መሆኑን፤
5. በዚች ዓለም ላይ የሚከሰቱ ነገሮች ሁሉ በአላህ ፈቃድ ብቻና ብቻ የሚከሰቱ መሆኑን፤
6. ትክክለኛ አማኝ ሁሉን ነገር ለአላህ ብቻ በመስጠት በእምነቱ ጠንካራ ምክንያቶችን ከፈፀመ በኋላ በሚያጋጥሙት ችግሮች አሚን ብሎ የሚቀበል እና አላህ እንዲፈፅም ያስገዳዳቸውን ገዴታዎች ሁሉ በአግባቡ የሚፈፅም መሆኑን፤
7. ኢስላም እምነቱም ሆነ ህግጋቱ ገር በመሆኑ የሰው ለጅ መፈፀም የሚገደደው የአቅሙን ያህል እንደሆነ፤
8. መልዕክተኛዉን መታዘዝ ልክ አላህን መታዘዝ እንደሆነ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የመቆጨት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (65)
## የፍች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አጦ-ጠላቅ)

سُورَةُ الطَّلَاقِ

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (12) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ إِذَا طَلَّقۡتُمُ ٱلنِّسَآءَ فَطَلِّقُوهُنَّ لِعِدَّتِهِنَّ وَأَحۡصُواْ ٱلۡعِدَّةَۖ وَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ رَبَّكُمۡۖ
لَا تُخۡرِجُوهُنَّ مِنۢ بُيُوتِهِنَّ وَلَا يَخۡرُجۡنَ إِلَّآ أَن يَأۡتِينَ بِفَٰحِشَةٖ مُّبَيِّنَةٖۚ وَتِلۡكَ حُدُودُ ٱللَّهِۚ
وَمَن يَتَعَدَّ حُدُودَ ٱللَّهِ فَقَدۡ ظَلَمَ نَفۡسَهُۥۚ لَا تَدۡرِي لَعَلَّ ٱللَّهَ يُحۡدِثُ بَعۡدَ ذَٰلِكَ أَمۡرٗا ١

1. አንተ ነብይ ሆይ፣ ሴቶችን መፍታት ባሰባችሁ ጊዜ፤ ለኢዳቸው ፍቱዋቸው፤ ኢዳንም ቁጠሩ፤* ጌታችሁን አላህን ፍሩ፤ ግልፅ የሆነችን ጠያፍ ካልሰሩ በስተቀር ከቤቶቻቸው አታስወጧቸው። አይውጡም፤ ይህችም የአላህ ህግጋት ናት። የአላህንም ህግጋት የተላለፈ ሰው በእርግጥ ነፍሱን በደለ፤ ከዚህ (ፍች) በኋላ እንደገና አላህ (የመማለስ) ነገር ምናልባት ያመጣ እንደሆነ አታውቅም።

* ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላ ኢብኑ ዑመር እንዳስተላፉት በሕይወት ሳሉ በአንድ ወቅት ዐብደላህ ሚስቶታቸውን የወር አበባ ላይ እያለች ፈቷት። ዑመርም ይህን አስመልክተው ነብዩን (ﷺ) ጠየቋቸው። የአላህ መልዕክተኛም:- «እንዲመልሳት አዘዘ» ከወር አበባ ደምም ጠርታ አሁንም የወር አበባ ተመልክታ እስከምትጠራ አብሮ እንዲያኖራትም ንገረው። ከዚያም በኋላ ምንም ሳይነካት ግንኙነት ሳይፈፅም በፊት ከፈለገ ያስቀምጣት ከፈለገ ደግሞ ይፍታታ። ይህ አላህ ያዘዘውና አንዲት ሴት ስትፈታ ልትከተለው ያስቀመጠው የጊዜ ገደብ ነው» አሉ።

فَإِذَا بَلَغۡنَ أَجَلَهُنَّ فَأَمۡسِكُوهُنَّ بِمَعۡرُوفٍ أَوۡ فَارِقُوهُنَّ بِمَعۡرُوفٖ وَأَشۡهِدُواْ ذَوَيۡ عَدۡلٖ
مِّنكُمۡ وَأَقِيمُواْ ٱلشَّهَٰدَةَ لِلَّهِۚ ذَٰلِكُمۡ يُوعَظُ بِهِۦ مَن كَانَ يُؤۡمِنُ بِٱللَّهِ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡأٓخِرِۚ وَمَن
يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مَخۡرَجٗا ٢ وَيَرۡزُقۡهُ مِنۡ حَيۡثُ لَا يَحۡتَسِبُۚ وَمَن يَتَوَكَّلۡ عَلَى ٱللَّهِ فَهُوَ
حَسۡبُهُۥٓۚ إِنَّ ٱللَّهَ بَٰلِغُ أَمۡرِهِۦۚ قَدۡ جَعَلَ ٱللَّهُ لِكُلِّ شَيۡءٖ قَدۡرٗا ٣

**2-3.** ጊዜያቸውንም ለመዳረስ በተቃረቡ ጊዜ በመልካም ያዙዋቸው፤ ወይም በመልካም ተለያዩዋቸው፤ ከናንተም ውስጥ ሁለት የትክክለኛነት ባለቤቶችን አስመስክሩ፤ ምስክርነትንም ለአላህ አስተካክሉ፤ ይሃችሁ በአላህና በመጨረሻ ቀን የሚያምን የሆነ ሰው ሁሉ በእርሱ ይገሰፀበታል፤ አላህንም የሚፈራ ሰው ለእርሱ መውጫን ያደርግለታል። ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፤ በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው። አላህ ፈቃዱን አድራሽ ነው። አላህ ለነገሩ ሁሉ የተወሰነ ጊዜን በእርግጥ አድርጓል።

ከፍች ምዕራፍ ከ (2-3) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አውፍ ቢን ማሊክ ልጁ በጠላቶች ተማርካ ስለነበር እናቱ አዘነች። ምን ይመክሩኛል? በማለት ነብዩን (ﷺ) ስለጠየቀ፡- ታገስ አላህን ፍራ። አንተም ሆንክ እናቱ ላሀውለ ወላቁወተ ኢላቢላህ የሚለውን አብዙ። ብለውት ወደ ቤቱ ተመልሶ ለሚስቱ የተነገረውን ነገራት። እሷም በጣም ጥሩ ነው የተባልነው አለች። የተባሉትን ሲተገብሩ ሳለ ተዘናግቶ እያለ ልጃቸው አራት ሺህ ፍየሎችን ነድቶ ይዞ ስለመጣ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

وَٱلَّٰٓـِٔي يَئِسۡنَ مِنَ ٱلۡمَحِيضِ مِن نِّسَآئِكُمۡ إِنِ ٱرۡتَبۡتُمۡ فَعِدَّتُهُنَّ ثَلَٰثَةُ أَشۡهُرٖ
وَٱلَّٰٓـِٔي لَمۡ يَحِضۡنَۚ وَأُوْلَٰتُ ٱلۡأَحۡمَالِ أَجَلُهُنَّ أَن يَضَعۡنَ حَمۡلَهُنَّۚ
وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يَجۡعَل لَّهُۥ مِنۡ أَمۡرِهِۦ يُسۡرٗا ٤

**4.** እነዚያም ከሴቶቻችሁ ከአደፍ (ከወር አበባ) ያቋረጡት በዒዳቸው ህግ ብትጠራጠሩ ዒዳቸው ሶስት ወር ነው። እነዚያም ገና አደፍን ያላዩ ሴቶች (ዒዳቸው እንደዚሁ ነው)። የእርግዝና ባለቤቶችም ጊዜያቸው እርጉዛቸውን መውለድ ነው፤ አላህንም የሚፈራ ሰው ከነገሩ ሁሉ ለእርሱ መግራትን ያደርግለታል።

ከፍች ምዕራፍ (4) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በአልበቀራ (222) ኛ ቁጥር ላይ ያለው አንቀፅ ሲወርድ ኻሊድ ቢን ዑመር ቢን አልጁምዐ ቢን ቀይስ አል አንሳሪ የተባለ ሶሀቢ ለነብዩ (ﷺ) የወር አበባ የማታይ አሮጊት የወር አበባ ያላየች ህፃንና እርጉዝ ሴት እንዴት ሊሆን ነው ኢዳዋን የምትቆጥረው? በዚህ ህግ አልተጠቃለሉም እየተባለ በመዲና ሴቶች ዘንድ እየተወራ ነው ብሎ ሲጠይቃቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

ذَٰلِكَ أَمۡرُ ٱللَّهِ أَنزَلَهُۥٓ إِلَيۡكُمۡۚ وَمَن يَتَّقِ ٱللَّهَ يُكَفِّرۡ عَنۡهُ سَيِّـَٔاتِهِۦ وَيُعۡظِمۡ لَهُۥٓ أَجۡرًا ٥

**5.** ይህ የአላህ ፍርድ ነው። ወደ እናንተ አወረደው፤ አላህንም የሚፈራ ሰው ሁሉ ኃጢአቶችን ከርሱ ይሰርዝለታል። ምንዳንም ለእርሱ ያተልቅለታል።

أَسۡكِنُوهُنَّ مِنۡ حَيۡثُ سَكَنتُم مِّن وُجۡدِكُمۡ وَلَا تُضَآرُّوهُنَّ لِتُضَيِّقُواْ عَلَيۡهِنَّۚ وَإِن كُنَّ أُوْلَٰتِ حَمۡلٖ فَأَنفِقُواْ عَلَيۡهِنَّ حَتَّىٰ يَضَعۡنَ حَمۡلَهُنَّۚ فَإِنۡ أَرۡضَعۡنَ لَكُمۡ فَـَٔاتُوهُنَّ أُجُورَهُنَّ وَأۡتَمِرُواْ بَيۡنَكُم بِمَعۡرُوفٖۖ وَإِن تَعَاسَرۡتُمۡ فَسَتُرۡضِعُ لَهُۥٓ أُخۡرَىٰ ٦ لِيُنفِقۡ ذُو سَعَةٖ مِّن سَعَتِهِۦۖ وَمَن قُدِرَ عَلَيۡهِ رِزۡقُهُۥ فَلۡيُنفِقۡ مِمَّآ ءَاتَىٰهُ ٱللَّهُۚ لَا يُكَلِّفُ ٱللَّهُ نَفۡسًا إِلَّا مَآ ءَاتَىٰهَاۚ سَيَجۡعَلُ ٱللَّهُ بَعۡدَ عُسۡرٖ يُسۡرٗا ٧

**6-7.** ከችሎታችሁ ከተቀመጣችሁበት ስፍራ አስቀምጧቸው። በእነርሱም ላይ ልታጣብቡ አትጉዷቸው። የእርግዝና ባለቤቶችም ቢሆኑ እርጉዛቸውን እስኪወልዱ ድረስ በእነርሱ ላይ ቀልቡ ለእናንተም ልጆቻችሁን ቢያጠቡላችሁ የልፋት ዋጋቸውን ስጧቸው። በመካከላችሁም በመልካም ነገር ተመካከሩ፤ ብትቸጋገሩም ለእርሱ ሌላ (ሴት) ታጠባለታለች። የችሎታ ባለቤት በችሎታው ልክ ይቀልብ፤ በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጠበበበት ሰው አላህ ከሰጠው ይቀልብ ነፍስን የሰጣትን ያህል እንጂ አያስገድድም። አላህ ከችግር በኋላ ምቾትን በእርግጥ ያደርጋል።

وَكَأَيِّن مِّن قَرۡيَةٍ عَتَتۡ عَنۡ أَمۡرِ رَبِّهَا وَرُسُلِهِۦ فَحَاسَبۡنَٰهَا حِسَابٗا شَدِيدٗا وَعَذَّبۡنَٰهَا عَذَابٗا نُّكۡرٗا ٨ فَذَاقَتۡ وَبَالَ أَمۡرِهَا وَكَانَ عَٰقِبَةُ أَمۡرِهَا خُسۡرًا ٩

**8-9.** ከከተማም መካከል ከጌታቸው እና ከመልዕክተኞች ትዕዛዝ ያመፁ በመሆናቸው፤ ብርቱን ቁጥጥር የተቆጣጠርናቸዉና መጥፎንም ቅጣት የቀጣናቸው ብዙ ናቸው። የነገራቸዉንም ቅጣት ቀመሱ። የነገራቸዉም መጨረሻ ኪሳራ ሆነ።

أَعَدَّ ٱللَّهُ لَهُمۡ عَذَابٗا شَدِيدٗاۖ فَٱتَّقُواْ ٱللَّهَ يَٰٓأُوْلِي ٱلۡأَلۡبَٰبِ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْۚ قَدۡ أَنزَلَ ٱللَّهُ إِلَيۡكُمۡ ذِكۡرٗا ١٠ رَّسُولٗا يَتۡلُواْ عَلَيۡكُمۡ ءَايَٰتِ ٱللَّهِ مُبَيِّنَٰتٖ لِّيُخۡرِجَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ مِنَ ٱلظُّلُمَٰتِ إِلَى ٱلنُّورِۚ وَمَن يُؤۡمِنۢ بِٱللَّهِ وَيَعۡمَلۡ صَٰلِحٗا يُدۡخِلۡهُ جَنَّٰتٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ قَدۡ أَحۡسَنَ ٱللَّهُ لَهُۥ رِزۡقًا ١١

**10-11.** አላህ ለእነርሱ ብርቱ ቅጣትን አዘጋጀ። እናንተም በአላህ ያመናችሁ የአእምሮ ባለ ቤቶች ሆይ፣ አላህን ፍሩ፤ አላህ ወደ እናንተ ግሳጼን በእርግጥ አወረደ፤ መልዕክተኛን ላከ። እነዚያን ያመኑትንና መልካሞችን የሰሩትን ከጨለማዎች ወደ ብርሃን ያወጣ ዘንድ የአላህን አንቀፆች ገላጮች ሲሆኑ

በእናንተ ላይ የሚያነብላችሁን ላከ። በአላህም አንቀፆች የሚያምን መልካምን ስራ የሚሰራም ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸው ዘለዓለም ዘውታሪዎች ሲሆኑ ያስገባዋል አላህ ለርሱ ሲሳይን በእርግጥ አሳመረ።

ٱللَّهُ ٱلَّذِى خَلَقَ سَبْعَ سَمَٰوَٰتٍ وَمِنَ ٱلْأَرْضِ مِثْلَهُنَّ يَتَنَزَّلُ ٱلْأَمْرُ بَيْنَهُنَّ لِتَعْلَمُوٓا۟ أَنَّ ٱللَّهَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ وَأَنَّ ٱللَّهَ قَدْ أَحَاطَ بِكُلِّ شَىْءٍ عِلْمًۢا ﴿١٢﴾

**12.** አላህ ያ ሰባትን ሰማያት የፈጠረ ነው። ከምድርም መሰላቸውን (ፈጥሯል)፤* በመካከላቸውም ትዕዛዙ ይወርዳል። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ መሆኑን አላህም በነገሩ ሁሉ በእውቀት ያካበበ መሆኑን ታውቁ ዘንድ (ይህንን አሳወቃችሁ)።

* ሰማያትም ሆነ ምድር ሰባት እንደሆኑና የሚያመለክት ነው። የሰማይ ሰባትነት በሱረቱል ሙልክ (3) ኛ አንቀፅም ተወስቷል። ከአንዱ ሰማይ እስከ ሁለት ሰማይ ከሁለት እስከ ሶስት ያለው እርቀት የአምስት መቶ አመት ያህል የሚያስኬድ መሆኑን የሰማይ ጉዟቸዉን በገለፁበት ሐዲስ ገልፀዋል። ምድርን በተመለከተ ብዙ ልዩነት፤ ጭቅጭቅና ክርክር ያለበት ቢሆንም ኢብኑ ዐባስ (መሰላቸውን) ማለት በቁጥርም ሆነ በአፈጣጠር በአጠቃላይ ሰማይን የሚመስል ማለት ነው ሲሉ፤ ሌሎች ደግሞ በቁጥር ብቻ ነው እንጂ እርቀታቸዉን በተመለከተ እንደሽንኩርት ልጣጮች ነው ያሉም አሉ። ሰባት የመሆኑ ጉዳይ በቁርኣን ባይገለፅም (በዚያ ስንዝር መሬትን የቀማ...) በሚለው ሐዲስና ነቢዩ ሙሳ (ጌታዬ አንተን የምለምንበት ስጠኝ) ባሉበት ሐዲስ ተነግሯል። ስለዚህ ቁጥሩን ተቀብለን ሁኔታውን ለአላህ መስጠት ይኖርብናል።

**ከፍች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-12) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ፍቺ መፈፀም ያለበት ለፍቺ በሚያበቃ ምክንያት መሆኑን፤
2. እርጉዝ ሳትሆን ባሏ የሞተባት አራት ወር ከአስር ቀን መቁጠር ያለባተ መሆኑን፤
3. እርጉዝ ሆና ባሏ የሞተባት እሱ ከሞተ አስከትወልድ ብቻ መጠበቋ፤
4. በህጻንነት ወይም በእርጅና ምክንያት የወር አበባ የማታይ ሴት፤
5. ስትፈታ ሶስት ወራትን መቁጠር እንዳለባት።
6. የወር አበባ የማታይ ከሆነች ከተፈታችበት ጡሃራ ጀምሮ ሶስት ጠሃራ መቁጠር ያለባት መሆኑን፤
7. ቀለብም ሆነ መኖሪያ የሚለው በራሱ በሰውየው አቅም የሚወሰን መሆኑን፤
8. የነብይነትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
9. በአላህ ዘንድ የነብዩን ክብር ከፍተኝነትና ትልቅነት፤
10. በአላህ ዘንድ የአቡበክር ሲድቅን ክብር ከፍተኝነት፤
11. ሚስትንና ልጅን መንከባከብ እንደሚገባ፤
12. ወንጀል የሰራ ሁሉ በቶሎ አላህን ይቅርታ መጠየቅ እንዳለበት፡
13. ከካሀዲያንን በጦር አስመሳዮችን በምላስ መዋጋት ግዴታ መሆኑን፤
14. ከሃዲ በአኼራ በምንም አይነት ተጠቃሚ እንዳልሆነ፤
15. አማኝ በከሃዲ ዘመዱ ምክንያት በምንም እንደማይጎዳ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የፍች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (66)
# እርም የማድረግ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አትተህሪም)

سُورَةُ التَّحْرِيمِ

የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (12) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ لِمَ تُحَرِّمُ مَآ أَحَلَّ ٱللَّهُ لَكَۖ تَبۡتَغِي مَرۡضَاتَ أَزۡوَٰجِكَۚ وَٱللَّهُ غَفُورٞ رَّحِيمٞ ۝١

**1.** አንተ ነብይ ሆይ፣ አላህ ለአንተ የፈቀደልህን ነገር ሚስቶችህን ማስወደድን የምትፈልግ ስትሆን (ባንተ ላይ) ለምን እርም ታደርጋለህ፤ አላህ እጅግ መሀሪና አዛኝ ነው።

ከእርም የማድረግ ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) የልጅ እናታቸውን ማሪያን በአይሻ ቀን በሌሊቱ ሚስታቸው በሀፍሷ ቤት ይዘዋት ገብተው ሀፍሷ ስላገኟቸው ተቆጥተው ከሌሎች ሴቶች ቤት የማያደርጉትን እኔ ቤት ያደረጉት ስለናቁኝ ነው በማለት ሲያማርሩ አይደልም ይህን ጉዳይ ለአይሻ አትንገሪያት። እሷም ከዛሬ በኋላ በእኔ ላይ እርም ናት አሏት። እሷ ሰራተኛ አይደለችም እንዴት ሀራም ትሆናለች ስትላቸው። በፍፁም ከዚህ በኋላ አልቀርባትም ባይሆን ለማንም አትንገሪ ብለዋት ሳለ ለአይሻ ነገረቻቸው። ነብዩ (ﷺ) ይህን ማድረጋቸውን በአይሻ በኩል ሲሰሙ በዚህ ጊዜ ለአንድ ወር ወደ ሴቶቻቸው ላይቀርቡ ማሉና (29) ሌሊት ራቋቸው። ከዚያም ይህ አንቀፅ ሁኔታው አግባብ እንዳልነበረ ለማስተማር ይህ አንቀፅ ወረደ። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

قَدۡ فَرَضَ ٱللَّهُ لَكُمۡ تَحِلَّةَ أَيۡمَٰنِكُمۡۚ وَٱللَّهُ مَوۡلَىٰكُمۡۖ وَهُوَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡحَكِيمُ ۝٢

**2.** አላህ ለእናንተ የመሐሎቻችሁን መፍቻ ደነገገላችሁ፤ አላህ ረዳታችሁ ነው። እርሱም አዋቂና ጥበበኛ ነው።

وَإِذۡ أَسَرَّ ٱلنَّبِيُّ إِلَىٰ بَعۡضِ أَزۡوَٰجِهِۦ حَدِيثٗا فَلَمَّا نَبَّأَتۡ بِهِۦ وَأَظۡهَرَهُ ٱللَّهُ عَلَيۡهِ عَرَّفَ بَعۡضَهُۥ
وَأَعۡرَضَ عَنۢ بَعۡضٖۖ فَلَمَّا نَبَّأَهَا بِهِۦ قَالَتۡ مَنۡ أَنۢبَأَكَ هَٰذَاۖ قَالَ نَبَّأَنِيَ ٱلۡعَلِيمُ ٱلۡخَبِيرُ ۝٣

**3.** ነብዩ ከሚስቶቹ ወደ አንዷ ወሬን በመሰጠረ ጊዜ (አስታውስ)። እርሱንም በነገረችና አላህ እርሱን ማውራቷን ባሳወቀው ጊዜ ከፊሉን አሳወቀ፤ ከፊሉንም ተወ፤ በእርሱም ባወራት ጊዜ ይህን ማን ነገረህ? አለች፤ አዋቂው እና ውስጠ አዋቂው ነገረኝ አላት።

إِن تَتُوبَآ إِلَى ٱللَّهِ فَقَدْ صَغَتْ قُلُوبُكُمَاۖ وَإِن تَظَٰهَرَا عَلَيْهِ فَإِنَّ ٱللَّهَ هُوَ مَوْلَىٰهُ وَجِبْرِيلُ
وَصَٰلِحُ ٱلْمُؤْمِنِينَۖ وَٱلْمَلَٰٓئِكَةُ بَعْدَ ذَٰلِكَ ظَهِيرٌ ﴿٤﴾ عَسَىٰ رَبُّهُۥٓ إِن طَلَّقَكُنَّ أَن يُبْدِلَهُۥٓ أَزْوَٰجًا
خَيْرًا مِّنكُنَّ مُسْلِمَٰتٍ مُّؤْمِنَٰتٍ قَٰنِتَٰتٍ تَٰٓئِبَٰتٍ عَٰبِدَٰتٍ سَٰٓئِحَٰتٍ ثَيِّبَٰتٍ وَأَبْكَارًا ﴿٥﴾

4-5. (ሁለታችሁም) ወደ አላህ ብትመለሱ ልቦቻችሁ በእርግጥ ተዘንብለዋልና (ትስማማላችሁ)። በእርሱ (ጥቃት ላይ) ብትረዳዱ ግን አላህና ጅብሪልም ከምዕመናንም መልካሞቹ፤ እርሱ ረዳቶች ናቸው። ከዚህም በኋላ መላዕክቶች ረዳቶች ናቸው። ሁላችሁንም ቢፈታችሁ ከናንተ የበለጡ ሚስቶች ሙስሊሞች፤ አማኞች፤ ታዛዦች፤ ተፀፃቾች፤ ለአላህ ተገዢዎች፣ ጿሚዎች፣ ባለ ፈቶች፣ ደናግልም የሆኑትን ጌታው ሊለውጠው ይከጀላል።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ قُوٓا۟ أَنفُسَكُمْ وَأَهْلِيكُمْ نَارًا وَقُودُهَا ٱلنَّاسُ وَٱلْحِجَارَةُ عَلَيْهَا
مَلَٰٓئِكَةٌ غِلَاظٌ شِدَادٌ لَّا يَعْصُونَ ٱللَّهَ مَآ أَمَرَهُمْ وَيَفْعَلُونَ مَا يُؤْمَرُونَ ﴿٦﴾

6. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ነፍሶቻችሁና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ደንጋዩች ከሆነች እሳት ጠብቁ፤ በእርሷ ላይ ጨካኝና ኃይለኛ የሆኑ መላዕክት አሉ። አላህን ያዘዛቸውን ነገር በመጣስ አያምፁም፤ የሚታዘዙትን ሁሉ ይሰራሉ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ كَفَرُوا۟ لَا تَعْتَذِرُوا۟ ٱلْيَوْمَۖ إِنَّمَا تُجْزَوْنَ مَا كُنتُمْ تَعْمَلُونَ ﴿٧﴾

7. እናንተ በአላህ የካዳችሁ ሰዎች ሆይ፣ ዛሬ አታመካኙ፤ የምትመነዱት ያንን ትሰሩት የነበራችሁትን ብቻ ነው (ይባላሉ)።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ تُوبُوٓا۟ إِلَى ٱللَّهِ تَوْبَةً نَّصُوحًا عَسَىٰ رَبُّكُمْ أَن يُكَفِّرَ عَنكُمْ
سَيِّـَٔاتِكُمْ وَيُدْخِلَكُمْ جَنَّٰتٍ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ يَوْمَ لَا يُخْزِى ٱللَّهُ ٱلنَّبِىَّ وَٱلَّذِينَ
ءَامَنُوا۟ مَعَهُۥۖ نُورُهُمْ يَسْعَىٰ بَيْنَ أَيْدِيهِمْ وَبِأَيْمَٰنِهِمْ يَقُولُونَ رَبَّنَآ أَتْمِمْ لَنَا نُورَنَا وَٱغْفِرْ لَنَآۖ
إِنَّكَ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ قَدِيرٌ ﴿٨﴾

8. እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ፣ ንፁህ የሆነችን ፀፀት በመፀፀት ወደ አላህ ተመለሱ፤ ጌታችሁ ከናንተ ኃጢአቶቻችሁን ሊሰርዝላችሁ፤ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች ሊያስገባችሁ ይከጀላልና። አላህ

ነብዩን እነዚያንም ከእርሱ ጋር ያመኑትን በማያሳፍርበት ቀን ብርሃናቸው በፊቶቻቸውና በቀኞቻቸው የሚሮጥ ሲሆን፡- ጌታችን ሆይ፣ ብርሃናችንን ሙላልን፤ ለእኛ ምህረትንም አድርግልን፤ አንተ በነገሩ ሁሉ ላይ ቻይ ነህና ይላሉ።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلنَّبِيُّ جَٰهِدِ ٱلْكُفَّارَ وَٱلْمُنَٰفِقِينَ وَٱغْلُظْ عَلَيْهِمْۚ وَمَأْوَىٰهُمْ جَهَنَّمُۖ وَبِئْسَ ٱلْمَصِيرُ ٩

9. አንተ ነብይ ሆይ! ከሓዲያን እና መናፍቃንን ታገል፤ በእነርሱም ላይ በርታ፤ መኖሪያቸውም ገሀነም ናት። ምን ትከፋም መመለሻ!

ضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا لِّلَّذِينَ كَفَرُوا۟ ٱمْرَأَتَ نُوحٍ وَٱمْرَأَتَ لُوطٍۖ كَانَتَا تَحْتَ عَبْدَيْنِ مِنْ عِبَادِنَا صَٰلِحَيْنِ فَخَانَتَاهُمَا فَلَمْ يُغْنِيَا عَنْهُمَا مِنَ ٱللَّهِ شَيْـًٔا وَقِيلَ ٱدْخُلَا ٱلنَّارَ مَعَ ٱلدَّٰخِلِينَ ١٠

10. አላህ ለእነዚያ ለካዱት ሰዎች የኑህን ሚስት እና የሉጥን ሚስት ምሳሌ አደረገ፤ ከባሮቻችን ከሆኑ ሁለት መልካም ባሪያዎች ስር ነበሩ ከዱዋቸውም ከአላህም ቅጣት ኑህና ሉጥ ከሚስቶቻቸው ምንም አልገፈተሩላቸውም ከገቢዎችም ጋር እሳትን ግቡ ተባሉ።

وَضَرَبَ ٱللَّهُ مَثَلًا لِّلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ ٱمْرَأَتَ فِرْعَوْنَ إِذْ قَالَتْ رَبِّ ٱبْنِ لِى عِندَكَ بَيْتًا فِى ٱلْجَنَّةِ وَنَجِّنِى مِن فِرْعَوْنَ وَعَمَلِهِۦ وَنَجِّنِى مِنَ ٱلْقَوْمِ ٱلظَّٰلِمِينَ ١١

11. ለእነዚያ ለአመኑትም ሁሉ የፈርዖንን ሚስት አላህ ምሳሌ አደረገ። ጌታዬ ሆይ፣ አንተ ዘንድ በገነት ውስጥ ለእኔ ቤት ገንባልኝ፤ ከፈርዖንና ከስራውም አድነኝ፤ ከበደለኞች ህዝቦችም አድነኝ ባለች ጊዜ።

وَمَرْيَمَ ٱبْنَتَ عِمْرَٰنَ ٱلَّتِىٓ أَحْصَنَتْ فَرْجَهَا فَنَفَخْنَا فِيهِ مِن رُّوحِنَا وَصَدَّقَتْ بِكَلِمَٰتِ رَبِّهَا وَكُتُبِهِۦ وَكَانَتْ مِنَ ٱلْقَٰنِتِينَ ١٢

12. የዒምራን ልጅ መርየምንም ያችን ብልቷን የጠበቀችውን (ምሳሌ አደረገ)። በእርሱም ውስጥ ከመንፈሳችን ነፋን። በጌታዋ ቃላትና በመጽሐፍቱም አረጋገጠች፤ ከወንድ* ታዛዥችም ነበረች።

✷ የተፍሲር ምሁራን እንደሚሉት ከሴት ታዛዦች ሳይል ከወንድ ታዛዦች ያለበትን ምክንያት ከዒባዳ ጥንካሬና ጌታን በመታዘዝ ወንዶች ይበልጥ ታዛዥ በመሆናቸው ነው ይላሉ። አዎ መርየም ከምርጥ ሴቶች አንዷ ናት። ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ከወንዶች ብዙዎች ሲሞሉ ከሴቶች ግን የሞሉት ጥቂቶች ናቸው»። እነሱም አስያ ቢንቱ ሙዛሂም፣ መርየም ቢንቱ ኢምራን፣ ኸዲጃ ቢንቱ ኹወይሊድ ናቸው» ብለዋል።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ደግሞ «አይሻ በሴቶች ላይ ያላቸው ብልጫ ሰሪድ የሚባል ምግብ ከሌሎች የምግብ አይነቶች ላይ ያለውን ብልጫ ያህል ነው»

ቲርሚዚ በዘገቡት ሀዲስ «ከዓለም ሴቶች መካከል ምርጦች መርየም ቢንቱ ኢምራን፣ ኸድጃ ቢንቱ ሁወይሊድ፣ ፋጡማ ቢንቱ ሙሐመድ፣ እናየፊርዓውን ባለቤት አስያ ቢንቱ ሙዛሂም ናቸው» ብለዋል።

**ከእርም ማድረግ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-12) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሓዲያንን በጦር ምናፍቃንን በአንደበት መታገል የሙስሊሞች ግዴታ መሆኑን፣
2. አንዱ በሌላው ጥፋት መጠየቅ የለም የሚለዉን ኢስላማዊ መመሪያ ማረጋገጥ፣
3. አማኞች ባላመኑ ቤተሰቦቻቸው ጥፋት እንደማይጠየቁ
4. ማንም ሰው ለማንም ብሎ አላህ ፈቀደለትን በራሱ ላይ እርም ማድረግ ተገቢ አለመሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ እርም የማድረግ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (67)
## የንግስና ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሙልክ)

سُورَةُ المُلْكِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (30) ናቸው።
### የሱረቱ አል ሙልክ መግቢያ

የተፍሲር ምሁራን እንደሚሉት ስምንት ስሞች አሉት። እነሱም፡-

1. አልሙልክ፤
2. ተባረከል ሙልኩ፤
3. ተባረከለዚቢየዲሂልሙልክ፤
4. አል ሙንጂያህ፤
5. አል ሙጃዲለህ፤
6. አልዋቂዐህ፤
7. አልማኒዐህ፤
8. አልመናዐህ ተብሎ ይሰየማል።

ጦበራኒ በዘገቡት ሐዲስ«በቁርኣን ዉስጥ ሰላሳ አንቀፆች ያሏት አንባቢዋን ተሟግታ ጀነት ያስገባች አለች እርሷም ተባረክ ናት» ብለዋል። ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ «በቁርኣን ዉስጥ ሰላሳ አንቀፆች ብቻ ያሏት አንባቢዋን ሸምግላ ጀነት ያሰገባች አለች እሷም ተባረክ ናት» ብለዋል። የቀብር ዋቢ እንደሆነች፤ ሁሉም ሰው ሊያውቃት እንደሚገባ፤ ቤተሰቦቻችንን ሁሉ ማስተማር እንዳለብን የሚመክሩ ሐዲሶችን ሸውካኒ በተፍሲር መፅሐፋቸው አዉስተዋል። የሀገራችን ሸኾችም አላህ ስራቸዉን ይውደደላቸዉና ይህን ለማስለመድ ብለው ሙሉ ቁርኣኑን ባን ሐፍዝ እንኳን ይህን ምእራፍና መሰሎችን በቃል ያስጠኑን ነበር።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

تَبَٰرَكَ ٱلَّذِي بِيَدِهِ ٱلۡمُلۡكُ وَهُوَ عَلَىٰ كُلِّ شَيۡءٖ قَدِيرٌ ١

**1.** *ያ ንግስና በእጁ የሆነው አላህ ችሮታው በዛ። እርሱም በሁሉም ነገር ላይ ቻይ ነው።

* ክፍል ሃያ አጠኝ

ٱلَّذِي خَلَقَ ٱلۡمَوۡتَ وَٱلۡحَيَوٰةَ لِيَبۡلُوَكُمۡ أَيُّكُمۡ أَحۡسَنُ عَمَلٗاۚ وَهُوَ ٱلۡعَزِيزُ ٱلۡغَفُورُ ٢

**2.** ያ የየትኛችሁ ስራ ይበልጥ ያማረ መሆኑን ሊሞክራችሁ ሞትንና ህይወትን የፈጠረ ነው። እርሱም አሸናፊና መሀሪ ነው።

ٱلَّذِى خَلَقَ سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ طِبَاقٗاۖ مَّا تَرَىٰ فِى خَلۡقِ ٱلرَّحۡمَٰنِ مِن تَفَٰوُتٖۖ فَٱرۡجِعِ ٱلۡبَصَرَ هَلۡ
تَرَىٰ مِن فُطُورٖ ٣ ثُمَّ ٱرۡجِعِ ٱلۡبَصَرَ كَرَّتَيۡنِ يَنقَلِبۡ إِلَيۡكَ ٱلۡبَصَرُ خَاسِئٗا وَهُوَ حَسِيرٞ ٤
وَلَقَدۡ زَيَّنَّا ٱلسَّمَآءَ ٱلدُّنۡيَا بِمَصَٰبِيحَ وَجَعَلۡنَٰهَا رُجُومٗا لِّلشَّيَٰطِينِۖ وَأَعۡتَدۡنَا لَهُمۡ عَذَابَ
ٱلسَّعِيرِ ٥ وَلِلَّذِينَ كَفَرُواْ بِرَبِّهِمۡ عَذَابُ جَهَنَّمَۖ وَبِئۡسَ ٱلۡمَصِيرُ ٦

**3-6.** ያ ሰባቱን ሰማያት የተነባበሩ ሆነው የፈጠረ ነው። በአል ረህማን አፈጣጠር ውስጥ ምንም ቅንጣት ያህል መዛነፍን አይታይም። ዓይንህንም መልስ። ከስንጥቆች አንዳችን ታያለህን? ከዚያ ብዙ ጊዜ ዓይንህን መላልስ። ዓይንህ ተዋርዶ (ተናንሶ)፤ እርሱም የደከመ ሆኖ ወደ አንተ ይመለሳል። ቅርቢቱን ሰማይም በእርግጥ በመብራቶች (በከዋክብት) አጌጥናት። ለሰይጣናትም መቀጥቀጫዎች አደረግናት፤ ለእርሱም (ለሰይጣኖች) ተንቀልቃይ የእሳትን ቅጣት አዘጋጀንላቸው። ለእነዚያም በጌታቸው (አላህን) ለካዱት የገሀነም ቅጣት አላቸው። መመለሻይቱም ገሀነም ከፋች!

إِذَآ أُلۡقُواْ فِيهَا سَمِعُواْ لَهَا شَهِيقٗا وَهِىَ تَفُورُ ٧ تَكَادُ تَمَيَّزُ مِنَ ٱلۡغَيۡظِۖ كُلَّمَآ أُلۡقِىَ فِيهَا
فَوۡجٞ سَأَلَهُمۡ خَزَنَتُهَآ أَلَمۡ يَأۡتِكُمۡ نَذِيرٞ ٨ قَالُواْ بَلَىٰ قَدۡ جَآءَنَا نَذِيرٞ فَكَذَّبۡنَا وَقُلۡنَا مَا نَزَّلَ
ٱللَّهُ مِن شَىۡءٍ إِنۡ أَنتُمۡ إِلَّا فِى ضَلَٰلٖ كَبِيرٖ ٩ وَقَالُواْ لَوۡ كُنَّا نَسۡمَعُ أَوۡ نَعۡقِلُ مَا كُنَّا فِىٓ
أَصۡحَٰبِ ٱلسَّعِيرِ ١٠ فَٱعۡتَرَفُواْ بِذَنۢبِهِمۡ فَسُحۡقٗا لِّأَصۡحَٰبِ ٱلسَّعِيرِ ١١

**7-11.** በውስጧ በተጣሉ ጊዜ እርሷ የምትፈላ ስትሆን ለእርሷ (እንደ አህያ) ማናፋትን ይሰማሉ። ከቁጭቷ የተነሳ ልትቆራረጥ ትቀርባለች። በውስጧ ጭፍሮች (ቡድኖች) በተጣሉ ቁጥር ዘበኞቿ (ስለዚህ ቀን) አስፈራሪ (ነብይ) አልመጣላችሁም ነበርን? በማለት ይጠይቋቸዋል። አይደለም በእርግጥ አስፈራሪ መጥቶልናል። አስተባበልንም። አላህም ምንንም አላወረደም። እናንተ (አውርዷል ስትሉ)፤ በትልቅ ስህተት ውስጥ እንጂ አይደላችሁም አልን ይላሉ። የምንሰማ ወይም የምናስብ በነበርን ኖሮ የነዳጅ እሳት ጓዶች ባልሆን ነበር ይላሉ። በኃጢአታቸውም ያምናሉ። ለእሳት ጓዶችም (ከእዝነት) መራቅ ተገባቸው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ يَخۡشَوۡنَ رَبَّهُم بِٱلۡغَيۡبِ لَهُم مَّغۡفِرَةٞ وَأَجۡرٞ كَبِيرٞ ١٢

**12.** እነዚያ ጌታቸውን በሩቁ የሚፈሩ ለእነርሱ ምህረትንና ታላቅ ምንዳ አለላቸው።

وَأَسِرُّواْ قَوْلَكُمْ أَوِ ٱجْهَرُواْ بِهِۦٓۖ إِنَّهُۥ عَلِيمُۢ بِذَاتِ ٱلصُّدُورِ ﴿١٣﴾
أَلَا يَعْلَمُ مَنْ خَلَقَ وَهُوَ ٱللَّطِيفُ ٱلْخَبِيرُ ﴿١٤﴾

**13-14.** (ሰዎች ሆይ!) ቃላችሁንም መስጥሩ። ወይም በእርሱ ጩሁ። እርሱ በልቦች ውስጥ ያለን ሁሉ አዋቂ ነው። የፈጠረ አምላክ እርሱ እውቀት ረቂቁ ውስጠ አዋቂው ሲሆን (ሚስጢርን) ሁሉ አያውቅምን?

ከንግስና ምዕራፍ (13) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የመካ ካሃዲያን እርስ በራሳቸው ድምፃችሁን ዝቅ አድርጋችሁ ተነጋገሩ። የሙሐመድ ጌታ እንዳይሰማችሁ ይሉ ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ)

هُوَ ٱلَّذِى جَعَلَ لَكُمُ ٱلْأَرْضَ ذَلُولًا فَٱمْشُواْ فِى مَنَاكِبِهَا وَكُلُواْ مِن رِّزْقِهِۦۖ
وَإِلَيْهِ ٱلنُّشُورُ ﴿١٥﴾ ءَأَمِنتُم مَّن فِى ٱلسَّمَآءِ أَن يَخْسِفَ بِكُمُ ٱلْأَرْضَ فَإِذَا هِىَ تَمُورُ ﴿١٦﴾
أَمْ أَمِنتُم مَّن فِى ٱلسَّمَآءِ أَن يُرْسِلَ عَلَيْكُمْ حَاصِبًاۖ فَسَتَعْلَمُونَ كَيْفَ نَذِيرِ ﴿١٧﴾
وَلَقَدْ كَذَّبَ ٱلَّذِينَ مِن قَبْلِهِمْ فَكَيْفَ كَانَ نَكِيرِ ﴿١٨﴾

**15-18.** እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው። በጋራዎቿና በመንገዶቿም ሂዱ። ከሲሳዮም ብሉ። (ኋላ) መመለሻችሁም ወደ እርሱ ብቻ ነው። በሰማይ ውስጥ ያለን ጌታ በእናንተ ምድርን ቢያሰምጥባችሁ ወዲያውም እርሷ የምታረገርግ ብትሆን ትተማመናላችሁን? (አትፈሩምን?)። ወይም በሰማይ ውስጥ ያለ ጌታ በእናንተ ላይ ጠጠርን ያዘለች ንፋስን ቢልክባችሁ ትተማመናላችሁን? (አትፈሩም?) ማስጠንቀቄም እንዴት እንደሆነ ወደ ፊት ታውቃላችሁ። እነዚያ ከእነርሱ በስተፊት የነበሩትም አስተባበሉ። ጥላቻየም እንዴት ነበር! (አስተዉል)፤

أَوَلَمْ يَرَوْاْ إِلَى ٱلطَّيْرِ فَوْقَهُمْ صَٰٓفَّٰتٍ وَيَقْبِضْنَۚ مَا يُمْسِكُهُنَّ إِلَّا ٱلرَّحْمَٰنُۚ
إِنَّهُۥ بِكُلِّ شَىْءٍۭ بَصِيرٌ ﴿١٩﴾

**19.** ከበላያቸው ሰልፍ ሰርተው ወዳሉ ወፎች አይመለከቱምን? ክንፎቻቸውን ያጥፋሉ። ከአልረህማን ሌላ የሚይዛቸው የለም። እርሱ ሁሉን ነገር አዋቂ ነው።

أَمَّنۡ هَٰذَا ٱلَّذِي هُوَ جُندٞ لَّكُمۡ يَنصُرُكُم مِّن دُونِ ٱلرَّحۡمَٰنِۚ إِنِ ٱلۡكَٰفِرُونَ إِلَّا فِي
غُرُورٍ ٢٠ أَمَّنۡ هَٰذَا ٱلَّذِي يَرۡزُقُكُمۡ إِنۡ أَمۡسَكَ رِزۡقَهُۥۚ بَل لَّجُّواْ فِي عُتُوّٖ وَنُفُورٍ ٢١
أَفَمَن يَمۡشِي مُكِبًّا عَلَىٰ وَجۡهِهِۦٓ أَهۡدَىٰٓ أَمَّن يَمۡشِي سَوِيًّا عَلَىٰ صِرَٰطٖ مُّسۡتَقِيمٖ ٢٢

**20-22.** በእውነት ያ እርሱ ከአልረህማን ሌላ የሚረዳችሁ ለእናንተ የሆነ ሰራዊት ማነው? ከሃዲያን በመታለል ውስጥ እንጂ በሌላ ላይ አይደሉም። ወይም ሲሳዮን ቢይዝባችሁ ያ ሲሳይን የሚሰጣችሁ ማነው? በእውነት እነርሱ በሞገድና በመደንበር ውስጥ ፀኑ። በፊቱ ላይ ተደፍቶ የሚሄድ ሰው ይበልጥ የተቀና ነውን? ወይስ በቀጥተኛው መንገድ ላይ ተስተካክሎ የሚሄድ?

قُلۡ هُوَ ٱلَّذِيٓ أَنشَأَكُمۡ وَجَعَلَ لَكُمُ ٱلسَّمۡعَ وَٱلۡأَبۡصَٰرَ وَٱلۡأَفۡـِٔدَةَۚ
قَلِيلٗا مَّا تَشۡكُرُونَ ٢٣ قُلۡ هُوَ ٱلَّذِي ذَرَأَكُمۡ فِي ٱلۡأَرۡضِ وَإِلَيۡهِ تُحۡشَرُونَ ٢٤
وَيَقُولُونَ مَتَىٰ هَٰذَا ٱلۡوَعۡدُ إِن كُنتُمۡ صَٰدِقِينَ ٢٥

**23-25.** እርሱ! ያ (አላህ) የፈጠራችሁ፤ ለእናተም መስሚያና ማያዎች፤ ልቦችንም ያደረገላችሁ ነው። ጥቂትንም አታመሰግኑምን በላቸው። እርሱ ያ በምድር ላይ የበተናችሁ ነው። ወደ እርሱም ትሰበሰባላችሁ በላቸው። እውነተኞችም እንደሆናችሁ ይህ ቀጠሮ መቼ ነው ተፈፃሚ የሚሆነው ይላሉ።

قُلۡ إِنَّمَا ٱلۡعِلۡمُ عِندَ ٱللَّهِ وَإِنَّمَآ أَنَا۠ نَذِيرٞ مُّبِينٞ ٢٦ فَلَمَّا رَأَوۡهُ زُلۡفَةٗ سِيٓـَٔتۡ وُجُوهُ ٱلَّذِينَ
كَفَرُواْ وَقِيلَ هَٰذَا ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تَدَّعُونَ ٢٧

**26-27.** እውቀቱ ከአላህ ዘንድ ብቻ ነው። እኔ ግልፅ አስፈራሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው። (ቅጣቱ) ቅርብ ሆኖ ባዩትም ጊዜ የእነዚያ የካዱት ሰዎች ፊቶች ይከፋሉ። ይህ ያ በእርሱ ትከራከሩበት የነበራችሁት ነው ይባላሉም።

قُلۡ أَرَءَيۡتُمۡ إِنۡ أَهۡلَكَنِيَ ٱللَّهُ وَمَن مَّعِيَ أَوۡ رَحِمَنَا فَمَن يُجِيرُ ٱلۡكَٰفِرِينَ مِنۡ عَذَابٍ أَلِيمٖ ٢٨

**28.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አያችሁን? እስኪ ንገሩኝ? አላህ ቢገድለኝ ከእኔ ጋር ያሉትንም (እንደዚሁ) ወይም በማቆየት ቢያዝንልን ከሓዲያንን ከአሳማሚ ቅጣት የሚያድን ማን ነው? በላቸው።

قُلْ هُوَ ٱلرَّحْمَٰنُ ءَامَنَّا بِهِۦ وَعَلَيْهِ تَوَكَّلْنَا ۖ فَسَتَعْلَمُونَ مَنْ هُوَ فِى ضَلَٰلٍ مُّبِينٍ ﴿٢٩﴾

**29.** እርሱ (እመኑበት የምላችሁ) አልረሀማን ነው። እኛ በእርሱ አመንን። በእርሱም ላይ ተጠጋን። ወደ ፊትም በግልፅ መሳሳት ውስጥ የሆነው እርሱ ማን እንደሆነ በእርግጥ ታውቃላችሁ በላቸው።

قُلْ أَرَءَيْتُمْ إِنْ أَصْبَحَ مَآؤُكُمْ غَوْرًا فَمَن يَأْتِيكُم بِمَآءٍ مَّعِينٍ ﴿٣٠﴾

**30.** አያችሁን (እስኪንገሩኝ?) ውሃችሁ ሰራጊ ቢሆን ወደ መሬት ቢሰርግ ፈሳሽን (ምንጭን) ውሃ የሚያመጣላችሁ ማን ነው በላቸው*።

*✳* *አንዳንድ ምሁራን ይህ አንቀፅ ሲነበብ አላህ የዓለማት ጌታ ያመጣዋል ማለቱ ተገቢ ነው ይላሉ። አንድ ከሃዲ ይህንን አባባል ሰምቶ መዶሻና ምሳሮች ያመጡታል ብሎ በመናገሩ ወዲያው አይኑ እንደጠፋ ይነገራል።*

**ከንግስና ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-30) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል፡-**

1. የአላህን ችሎታ በሚያመለክቱ ጉዳዩች ላይ መመራመር አስፈላጊ መሆኑን፤
2. ሞትና ህይወትን ከመፍጠር በስተጀርባ ያለውን ጥበብ መመራመር እንዳለብን፤
3. አላህ የፈጠራቸው ነገሮች ሁሉ በጥበብ የተሞሉና የሚደንቁ መሆናቸውን፤
4. ከሓዲያን ከሰይጣኖች ጋር በዱንያም የሚቀጡ ከመሆናቸውም አልፎ በአኼራም እሳት እንደሚጠብቃቸው፤
5. ከሓዲያንና ወንጀለኞች በትንሳኤ ዕለት ቅጣታቸውን ሲያዩ መፀፀት የማይጠቅማቸው ቢሆንም እንደሚፀፀቱ፤
6. አማኝ ሲሳይን ሲፈልግ ምክንያቶችን እየሰራ በጌታው ላይ በመመካት ሲሆን ከሃዲ ግን በምክንያቶች ላይ ብቻ የሚመካ መሆኑን፤
7. በራሪ አዕዋፍ ካፈጣጠራቸው አንስቶ እስከ መብበራቸው ድረስ አያሌ የአላህ ተዐምራት እንደሚታይባቸው፤
8. አላህ በሰዎች ላይ የዋላቸው ፀጋዎች ብዙ ቢሆኑም ከዋናዎቹ ዉስጥ ማየት፤ መስማት ማሰብ ጥቂቶቹ መሆናቸውን፤
9. ውሃ አላህ ለባሮቹ ከዋለላቸው ውለታዎች መካከል አንዱ በመሆኑ በእኛ ላይ መጠበቁ ግዴታ መሆኑን፤
10. ሙስሊም የሆነ ሰው ይህን በቃል ማጥናትና በየጊዜው ማንበብ እንዳለብንም እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የንግስና ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (68)
# የቀለም ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልቀለም)

سُورَةُ القَلَمِ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (52) ናቸው።
### የሱረቱ አል ቀለም መግቢያ

ይህ ምእራፍ ከነብዩ ሙሐመድ ላይ ከመከላከሉም በላይ እውነትን አጥብቀው እንዲይዙና ለምንም ሲሉ ለባጢል እንዳይንበረከኩ ስሜታቸውን ያነሳሳል። ሞራላቸውን ያጠነክራል። በአቋማቸው ላይ እንዲፀኑም አጥብቆ ይመክራል። በመኮች ላይ የደረሰውም ቅጣት በዚህ ምእራፍ ውስጥ ታሪካቸው በተተረከው ሰዎች ይመሰላል። አማኞችን ከአላህ ዘንድ የሚጠብቃቸውን ከፍተኛ አጅር በማስታወስ አብስሮ ከከሓዲያን ጋር ፈፅሞ እኩል እንደማይሆኑ በግልፅ ያስተምራል። በተጨማሪም ከሓዲያን ያለአግባብ ለራሳቸው አለን በማለት የሚኮፈሱትን ይቃወማል። የእነሱም መጨረሻ ምን እንደሚመስል አስፈራርቶ ነብዩን እንዲታገሱ በመመከርና ቁርኣንን የዐለም መገሰጫ እንደሆነ በማሞገስ መልእክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

نٓۚ وَٱلۡقَلَمِ وَمَا يَسۡطُرُونَ ١ مَآ أَنتَ بِنِعۡمَةِ رَبِّكَ بِمَجۡنُونٖ ٢ وَإِنَّ لَكَ لَأَجۡرًا غَيۡرَ
مَمۡنُونٖ ٣ وَإِنَّكَ لَعَلَىٰ خُلُقٍ عَظِيمٖ ٤ فَسَتُبۡصِرُ وَيُبۡصِرُونَ ٥ بِأَييِّكُمُ ٱلۡمَفۡتُونُ ٦
إِنَّ رَبَّكَ هُوَ أَعۡلَمُ بِمَن ضَلَّ عَن سَبِيلِهِۦ وَهُوَ أَعۡلَمُ بِٱلۡمُهۡتَدِينَ ٧

**1-7.** ኑን፣* በብዕር እምላለሁ በዚያም (መልአኮች) በሚጽፉት (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ በጌታህ ፀጋ ምክኒያት ዕብድ አይደለህም ለአንተም ከጌታህ የማይቋረጥ ምንዳ (የልፋት ዋጋ) በእርግጥ አለህ። አንተም በታላቅ ፀባይ ላይ ነህ። ወደ ፊት አንተም ታያለህ፤ እነርሱም ያያሉ፤ ዕብደት በማንኛችሁ እንዳለ (እብዱ ማን እንደሆነ)። ጌታህ ከመንገዱ የተሳሳተውንም ሆነ ወደ ቀናው መንገድ ተመሪዎችን አዋቂ ነውና።

✴ (እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ፊደሎች በሱረቱ አል በቀራህ በ1ኛው አንቀጽ ግርጌ ላይ እንደተጠቀሰው ከቁርኣን ታኣምራት (ሙዕጂዛህ) መካከል የሚጠቀሱ ሲሆን ትክክለኛ ፍቻቸውን አላህ ብቻ ነው የሚያውቀው)።

ከቀለም ምዕራፍ (2) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- የመካ ሰወች ነብዩን (ﷺ) እንደ እብድ ይቆጥሯቸው ስለ ነበር ለእነሱ የዉሼት ዘመቻ መልስ ይሆን ዘንድ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

فَلَا تُطِعِ ٱلْمُكَذِّبِينَ ﴿٨﴾ وَدُّواْ لَوْ تُدْهِنُ فَيُدْهِنُونَ ﴿٩﴾ وَلَا تُطِعْ كُلَّ حَلَّافٍ مَّهِينٍ ﴿١٠﴾
هَمَّازٍ مَّشَّآءِۭ بِنَمِيمٍ ﴿١١﴾ مَّنَّاعٍ لِّلْخَيْرِ مُعْتَدٍ أَثِيمٍ ﴿١٢﴾ عُتُلٍّ بَعْدَ ذَٰلِكَ زَنِيمٍ ﴿١٣﴾

**8-13.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስለዚህ ለአስተባባዮች ሁሉ አትታዘዝ። (አስተባባዮች) ብትመሳሰላቸውና እነርሱም ቢመሳሰሉህ ተመኙ። መሓለኛን፣ ወራዳን፣ ሰውን አነዋሪን፣ ነገር አሳባቂን፣ ለበጎ ነገር በጣም ከልካይን፣ ወሰን አላፊን፣ ኃጢአተኛን፣ ልበ ደረቅን ከዚህ ሁሉ በተጨማሪ የዝሙት ልጅ ዲቃላን ሰው (ሁሉ አትታዘዝ)።

أَن كَانَ ذَا مَالٍ وَبَنِينَ ﴿١٤﴾ إِذَا تُتْلَىٰ عَلَيْهِ ءَايَٰتُنَا قَالَ أَسَٰطِيرُ ٱلْأَوَّلِينَ ﴿١٥﴾
سَنَسِمُهُۥ عَلَى ٱلْخُرْطُومِ ﴿١٦﴾

**14-16.** የገንዘብና የልጆች ባለቤት በመሆኑ ያስተባብላል። በእርሱ ላይ አንቀጾቻችን በሚነበቡ ጊዜ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ናቸው ይላል። በአፍንጫው* ላይ በእርግጥ የሚነወርበት ምልክትን እናደርግበታለን።

* ይህ ሰው ወሊድ ኢብኑ ሙጊራ የተባለው የሙስሊሞች ጠላት ነው ተብሏል።

إِنَّا بَلَوْنَٰهُمْ كَمَا بَلَوْنَآ أَصْحَٰبَ ٱلْجَنَّةِ إِذْ أَقْسَمُواْ لَيَصْرِمُنَّهَا مُصْبِحِينَ ﴿١٧﴾ وَلَا يَسْتَثْنُونَ ﴿١٨﴾
فَطَافَ عَلَيْهَا طَآئِفٌ مِّن رَّبِّكَ وَهُمْ نَآئِمُونَ ﴿١٩﴾ فَأَصْبَحَتْ كَٱلصَّرِيمِ ﴿٢٠﴾ فَتَنَادَوْاْ
مُصْبِحِينَ ﴿٢١﴾ أَنِ ٱغْدُواْ عَلَىٰ حَرْثِكُمْ إِن كُنتُمْ صَٰرِمِينَ ﴿٢٢﴾ فَٱنطَلَقُواْ وَهُمْ يَتَخَٰفَتُونَ ﴿٢٣﴾
أَن لَّا يَدْخُلَنَّهَا ٱلْيَوْمَ عَلَيْكُم مِّسْكِينٌ ﴿٢٤﴾ وَغَدَوْاْ عَلَىٰ حَرْدٍ قَٰدِرِينَ ﴿٢٥﴾ فَلَمَّا رَأَوْهَا قَالُوٓاْ
إِنَّا لَضَآلُّونَ ﴿٢٦﴾ بَلْ نَحْنُ مَحْرُومُونَ ﴿٢٧﴾ قَالَ أَوْسَطُهُمْ أَلَمْ أَقُل لَّكُمْ لَوْلَا تُسَبِّحُونَ ﴿٢٨﴾ قَالُواْ
سُبْحَٰنَ رَبِّنَآ إِنَّا كُنَّا ظَٰلِمِينَ ﴿٢٩﴾ فَأَقْبَلَ بَعْضُهُمْ عَلَىٰ بَعْضٍ يَتَلَٰوَمُونَ ﴿٣٠﴾ قَالُواْ يَٰوَيْلَنَآ إِنَّا
كُنَّا طَٰغِينَ ﴿٣١﴾ عَسَىٰ رَبُّنَآ أَن يُبْدِلَنَا خَيْرًا مِّنْهَآ إِنَّآ إِلَىٰ رَبِّنَا رَٰغِبُونَ ﴿٣٢﴾ كَذَٰلِكَ ٱلْعَذَابُۖ
وَلَعَذَابُ ٱلْأٓخِرَةِ أَكْبَرُۚ لَوْ كَانُواْ يَعْلَمُونَ ﴿٣٣﴾

**17-33.** እኛ እነዚያን የአትክልቲቱን ባለቤቶች ማልደው ፍሬዋን ሊለቅሟት አላህ ቢሻ ሳይሉ በማሉ ጊዜ እንደሞከርን ሁሉ የመካን ሰዎች ሞከርናቸው። እነርሱ የተኙ ሆነውም ሳሉ ከጌታህ የሆነ ዟሪ በእርሷ ላይ ዞረባት። እንደ ሌሊት ጨለማ የከሰለች ሆና አነጋች (ከሰለች)። ያነጉም ሆነው ቆራጮች እንደ ሆናችሁ

ወደ እርሻችሁ ለመሄድ ማልዱ በማለት ተጠራሩ። እነርሱ የሚያሾካሾኩ ሆነው ሄዱም። ዛሬ በእናንተ ላይ ድሃ እንዳይገባት በማለትና ድሆችን በመከልከልም ላይ በሀሳባቸው ቻዮች ሆነው ማለዱ። ከዚያ ተቃጥላ ባዩዋት ጊዜ እኛ በእርግጥ ተሳሳቾች ነን አሉ። ይልቁንም እኛ ከአላህ የተከለከልን እደለ ቢሶች ነን አሉ። (ከመካከላቸው) ትክክለኛቸው (አስተዋያቸው)፦ ለእናንተ አላህን ለምን አታጠሩም (አታወሱም) አላልኳችሁም ነበርን? አለ። ሁላቸዉም ጌታችን ጥራት ይገባው፤ እኛ በዳዩች ነበርን አሉ። እርስ በራሳቸው የሚወቃቀሱም ሆነው ከፊሎቻቸው በከፊሉ ላይ መጡ። እርስ በእርስ ይወቃቀሱም ጀመር። ዋ፣ ጥፋታችን፣ እኛ ድንበር አላፊዎች ነበርን አሉ። ጌታችን ከእርሷ የተሻለን (አትክልት) ሊለውጠን ይከጀላል። እኛ ወደ ጌታችን ከጃዩች ነን አሉ። (የአላህ) ቅጣቱ ልክ እንደዚሁ ነው። የመጨረሻይቱም ዓለም ቅጣት ከዚህ የበለጠ ታላቅ ነው። የሚያውቁ ቢሆኑ ኖሮ ከዚህ ቅጣት (በተጠነቀቁ ነበር)።

إِنَّ لِلۡمُتَّقِينَ عِندَ رَبِّهِمۡ جَنَّٰتِ ٱلنَّعِيمِ ﴿٣٤﴾ أَفَنَجۡعَلُ ٱلۡمُسۡلِمِينَ كَٱلۡمُجۡرِمِينَ ﴿٣٥﴾
مَا لَكُمۡ كَيۡفَ تَحۡكُمُونَ ﴿٣٦﴾ أَمۡ لَكُمۡ كِتَٰبٞ فِيهِ تَدۡرُسُونَ ﴿٣٧﴾ إِنَّ لَكُمۡ فِيهِ لَمَا
تَخَيَّرُونَ ﴿٣٨﴾ أَمۡ لَكُمۡ أَيۡمَٰنٌ عَلَيۡنَا بَٰلِغَةٌ إِلَىٰ يَوۡمِ ٱلۡقِيَٰمَةِ إِنَّ لَكُمۡ لَمَا تَحۡكُمُونَ ﴿٣٩﴾
سَلۡهُمۡ أَيُّهُم بِذَٰلِكَ زَعِيمٌ ﴿٤٠﴾

**34-40.** ለጥንቁቆች በጌታቸው ዘንድ መጠቀሚያ ገነቶች አሏቸው። ሙስሊሞችን እንደ ከሓዲያን እናደርጋለን? (አናደርግም)። ለእናንተ ምን (አስረጂ) አላችሁ? እንዴት ትፈርዳላችሁ። በእውነቱ ለእናንተ በእርሱ የምታጠኑበት መጽሐፍ አላችሁን? በውስጡ ለእናንተ የምትመርጡት አላችሁ (የሚል)። ወይስ ለእናንተ የምትፈርዱት አላችሁ በማለት (ቃል ኪዳን የገባንላችሁ) እስከ ትንሳኤ ቀን ደራሽ የሆኑ መሐላዎች ለእናንተ በእኛ ላይ አሏችሁን? በዚህ ማንኛቸውም ተያዥ እንደሆነ ጠይቃቸው።

أَمۡ لَهُمۡ شُرَكَآءُ فَلۡيَأۡتُواْ بِشُرَكَآئِهِمۡ إِن كَانُواْ صَٰدِقِينَ ﴿٤١﴾ يَوۡمَ يُكۡشَفُ عَن سَاقٖ وَيُدۡعَوۡنَ
إِلَى ٱلسُّجُودِ فَلَا يَسۡتَطِيعُونَ ﴿٤٢﴾ خَٰشِعَةً أَبۡصَٰرُهُمۡ تَرۡهَقُهُمۡ ذِلَّةٞۖ وَقَدۡ كَانُواْ يُدۡعَوۡنَ إِلَى
ٱلسُّجُودِ وَهُمۡ سَٰلِمُونَ ﴿٤٣﴾ فَذَرۡنِي وَمَن يُكَذِّبُ بِهَٰذَا ٱلۡحَدِيثِۖ سَنَسۡتَدۡرِجُهُم مِّنۡ حَيۡثُ
لَا يَعۡلَمُونَ ﴿٤٤﴾ وَأُمۡلِي لَهُمۡۚ إِنَّ كَيۡدِي مَتِينٌ ﴿٤٥﴾

**41-45.** ወይስ ለእነርሱ (በፍርዳቸው ተስማሚ) ተጋሪዎች አሏቸውን? እውነተኞችም እንደሆኑ ተጋሪዎቻቸውን ያምጡ። (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) ያን ከፉ ቀን ባት* የሚገለጥበትን፣ (ከሓዲያን) ወደ መስገድ የሚጠሩበትንና የማይችሉበትን ቀን (አስታውስ)። ዓይኖቻቸው የፈሩ፤ ውርደት የምትሸፍናቸው ሲሆኑ (ወደ ስግደት የሚጠሩበትን)። እነርሱ (በምድረ ዓለም) ደህና ሆነው ሳሉ ወደ ስግድት በእርግጥ ይጠሩ ነበሩ። (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) በመሆኑም እኔን በዚህ ንግግር ከሚያስተባብሉት ሰዎች ጋር ተወኝ፤ (ለእነርሱ እኔ እበቃሃለሁ)። ከማያውቁት ስፍራ አዘናግተን እንይዛቸዋለን። እነርሱንም አዘገያቸዋለሁ። (ዘዴዬ) ብቀላዬ ብርቱ ነውና።

* አላህ በሰዎች መካከል ዉሳኔን ለመስጠት ሲመጣ በማንም ሆነ በምንም ሳንመስል ማመን ያለብን ይህና ይህን መሰል የአላህን ባህሪና ስሞች የሚናገሩ የቁርኣን አናቅጾችና ሐዲሶች ተፍሲር በተመለከተ አላህን ከማንም ከምንም ፍጡር ጋር ሳናመሳስልና አላህን ከጉድለት በማጥራት በሰለፎች ግንዛቤና አረዳድ እናስቀምጣለን እዚህ ላይ በጣም ልንጠነቀቅ የሚገባው ነገር ነኛ እንዴት? (ከይፍ?) እና ለምን? የሚሉ ጥያቄዎች ሁሉ በፍጹም የተከለከሉ ናቸው 2ኛ አላህ በማንም በምንም አይመሳሰልም በዚህ ዙሪያ በሰፊው ለመረዳት በሱረቱ አል አዕራፍ (54) አንቀጽ ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ ተመልከት።

أَمْ تَسْـَٔلُهُمْ أَجْرًا فَهُم مِّن مَّغْرَمٍ مُّثْقَلُونَ ﴿٤٦﴾

**46.** (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ!) ወይንስ በእውነቱ (በማስተማርህ) ዋጋን እንዲከፍሉህ ትጠይቃቸዋለህን? ስለዚህ እነርሱ ከዕዳ የተከበዱ ናቸውን?

أَمْ عِندَهُمُ ٱلْغَيْبُ فَهُمْ يَكْتُبُونَ ﴿٤٧﴾

**47.** ወይስ ከእነርሱ ዘንድ የሩቁ ምስጢር እውቀት አለን? ስለዚህ እነርሱ ይፅፋሉን?

فَٱصْبِرْ لِحُكْمِ رَبِّكَ وَلَا تَكُن كَصَاحِبِ ٱلْحُوتِ إِذْ نَادَىٰ وَهُوَ مَكْظُومٌ ﴿٤٨﴾ لَّوْلَآ أَن تَدَٰرَكَهُۥ
نِعْمَةٌ مِّن رَّبِّهِۦ لَنُبِذَ بِٱلْعَرَآءِ وَهُوَ مَذْمُومٌ ﴿٤٩﴾ فَٱجْتَبَٰهُ رَبُّهُۥ فَجَعَلَهُۥ مِنَ ٱلصَّٰلِحِينَ ﴿٥٠﴾

**48-50.** (መልዕክተኞችን ሙሐመድ ሆይ)፣ ለጌታህ (ዉሳኔ) ፍርድ ታገስ። (በመበሳጨትና ባለ መታገስ) እንደ ዓሳው ባለቤት እንደ (ነብዩ ዩናስ) አትሁን። እርሱ በጭንቀት የተሞላ ሆኖ (ጌታውን) በተጣራ ጊዜ ከጌታው የሆነ ፀጋ ባላገኘው ኖሮ በምድረ በዳ ተወቃሽ ሆኖ በተጣለ ነበር። ጌታውም (በነብይነት) መረጠው። ከደጋጎችም አደረገው።

وَإِن يَكَادُ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ لَيُزْلِقُونَكَ بِأَبْصَٰرِهِمْ لَمَّا سَمِعُواْ ٱلذِّكْرَ وَيَقُولُونَ إِنَّهُۥ لَمَجْنُونٌ ﴿٥١﴾ وَمَا هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿٥٢﴾

**51-52.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እነሆ እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ቁርኣኑን በሰሙ ጊዜ በዓይኖቻቸው ሊጥሉህ (ሊያጠፉህ) ይቃረባሉ፤ እርሱም በእርግጥ እብድ ነውም ይላሉ። እርሱ (ቁርኣን) ግን ለዓለማት መገሰጫ (ገሳጭ) እንጂ ሌላ አይደለም።

**ከቀለም ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-52) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በእነዚህ አናቅፅ ውስጥ የተወገዙትን መጥፎ ባህሪያት ማውገዝና ሰዎች እንዲርቋቸው ማድረግ፤
2. የገንዘብና የልጅ መብዛት ለኩራት ምክንያት መሆኑን ገልፆ ከዚህ መሰል ተግባር መጠንቀቅ እንዳለብን ማስታወስ፤
3. በአላህ ተዐምራት ማስተባበልን ማውገዝና አስተባባዩችን ከመታዘዝና ከመመሳሰል መጠንቀቅ ግዴታ መሆኑን;
4. አላህ በብዕርና በፁሁፍ ስለማለ በፈለገው ነገር እንደሚምል፤
5. የሁሉ መፃፊያ የሆነው ብዕር ትልቅነትና ክብር እንዳለው፤
6. ቀደርን ተቀብሎ ማመንና መማር አስፈላጊ መሆኑን፤
7. ከነብዩ (ﷺ) መልካም ባህሪያት በጥቂቱ፤
8. የነብዩ (ﷺ) ባህሪ ሙሉዕነትን ማረጋገጥ፤
9. የቂያማ ዕለት ፍሬው ከገለባው፤ እውነትንም ከውሸት እንደሚለይ፤
10. ለሰው ልጆች በኸይርም ሆነ በሸር መፈተን ያለ ስለ መሆኑ፤
11. አላህ የሰው ልጆችን ሲፈጥር የየራሳቸው ባህሪና የተለየ ችሎታ ባለቤቶች አድርጎ ነው። ሰዎች በተሰማሩበት ስራ ላይ ውጤታማ ሊሆኑ የሚችሉት በሙያዎችና በችሎታቸው ሲመደቡና በፍላጎታቸው ሲሰሩ ብቻ መሆኑን፤
12. እዚህ ላይ ሊታሰብቡት የሚገባ ነገር ቢኖር የአደር ባይነት አስመሳይነት መስሎ ኗሪነት ጉዳይ ነው። ሰዎች ከአደም ጀምሮ እስከ መጨረሻው የሰው ዘር ድረስ በመልክ አይመሳሰሉም። ታዲያ በአስተሳሰብ መመሳሰል እንዴት ሊኖር ይችላል። ብዙ ሰዎች የራሳቸውን ማንነት ወደ ጎን በመተው ሌላን ሰው ለመምሰል ሲጣጣሩ ይታያሉ። ይህ ሙከራ የማይሳካ ከንቱ ሙከራ ከመሆኑም በላይ የአላህን የተፈጥሮ ህግም ይቃረናል። ማንም ሰው የየራሱ የሆነ የግል ባህሪና ችሎታ ዝንባሌ እንዳለው፤
13. የአላህ ውለታዎች አለማመስገን እንደመካድ እንደሚቆጠር፤
14. ከነኚህ ሰዎች ታሪክ ብዙ ቁም ነገሮችን እንደምንማር፤
15. ማንም ሰው ለወደፊቱ አንድ ስራ ለመስራት ሲያስብ በአላህ ፈቃድ ከሆነ ማለት እንደሚገባ፤
16. የአላህ ችሎታ ከፍጡሮች ሁሉ በላይ መሆኑንና አላህ ሊያደርገው ያሰበውን ነገር የማንም ምክክር ጥንቃቄ ሊያድነው እንደማይችል፤
17. ከስህተት ታርሞ ከጥፋት መመለስ መፀፀት በኢስላም ከፍተኛ ደረጃ እንዳለው፤
18. የእኒህ ሰዎች ታሪክ በማንኛውም ነፍስ ላይ ሊደገም እንደማይችል፤

19. ትክክለኛ ሰው ማለት ሰዎችን ወደ አላህ የሚጠራና በአላህ የሚያስታውስ መሆኑን፤
20. አመፀኞች ከአማኖች ጋር በተግባርም ሆነ በምንዳ እንደማይስተካከሉ፤
21. አመፀኞችን ማውገዝና ማስረዳት፤
22. የቂያማ ቀን ለከሓዲያን የተዘጋጀው ችግርና መከራም ምን ያህል አስከፊ እንደሆነ፤
23. ሁሉን ነገር ለአላህ መስጠትና የሚወሰደው እርምጃ መጠባበቅ እንደሚገባ፤
24. ስለ ነብዩ ሙሃመድ (ﷺ) ትዕግስት፤
25. በዳዕዋ ስራ ላይ ክፍያ መውሰድ ክልክል ስለ መሆኑ፤
26. ለዳዕዋ ስራ ትዕግስት አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
27. ሙሽሪኮች ከነብዩ (ﷺ) ጋር የነበራቸው ሁኔታና ለሳቸው የነበራቸው ጥላቻና ምቀኝነት ይለጠፍባቸው የነበረው ስድብና መጥፎ ስም እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የቀለም ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (69)
## የአረጋጋጭቱ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሓቀህ)

سُورَةُ الحَاقَّةِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (52) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

ٱلۡحَآقَّةُ ١ مَا ٱلۡحَآقَّةُ ٢ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡحَآقَّةُ ٣

1-3. እውነትን አረጋጋጪቱ (ትንሳኤ)። አረጋጋጪቱም (እርሷ) ምንድን ናት!? (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አረጋግጪቱም ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?*

* ለነቢዩ ነው ይህ አባባል። እናም አቡ ዘመንይን የተባለ ዐሊም ሲናገሩ «ማ አድራከ» የተባለውን ሁሉ አላህ ያሳወቃቸው ነገርን ነው። «ማዩድሪከ» የተባሉት ግን ገና ያላሳወቃቸዉን ነው ብለዋል። የምታረጋግጠው ነገር ምን እንደሆነ መገመቱ ባይከብድም ምሁራን በዚህ ቦታ ለምሳሌ የጠቀሱትን መዝከሩ ይጠቅማል። ቀታዳህ ስራ ለሰሪው የሚከፈልበት ቀን ለማለት ነው ብለዋል። ሌሎችም አማኝ የእምነቱን ምናፌቅም የንፍቅናዉን ዋጋ የሚያየበት ቀን ማለት ነው ብለዋል።

كَذَّبَتۡ ثَمُودُ وَعَادُۢ بِٱلۡقَارِعَةِ ٤ فَأَمَّا ثَمُودُ فَأُهۡلِكُواْ بِٱلطَّاغِيَةِ ٥ وَأَمَّا عَادٞ فَأُهۡلِكُواْ بِرِيحٖ صَرۡصَرٍ عَاتِيَةٖ ٦ سَخَّرَهَا عَلَيۡهِمۡ سَبۡعَ لَيَالٖ وَثَمَٰنِيَةَ أَيَّامٍ حُسُومٗاۖ فَتَرَى ٱلۡقَوۡمَ فِيهَا صَرۡعَىٰ كَأَنَّهُمۡ أَعۡجَازُ نَخۡلٍ خَاوِيَةٖ ٧ فَهَلۡ تَرَىٰ لَهُم مِّنۢ بَاقِيَةٖ ٨

4-8. የሰሙድና የዓድ ህዝቦች በቆርቋሪይቱ (ትንሳኤ) ቀን አስተባበሉ። የሰሙድ ህዝቦችማ ወሰን በሌላት ነፋስ ጩኸት ተጠፉ*። የዓድ ህዝቦችማ በኃይል በምትንሻሻ ብርቱ ነፋስ ተጠፉ። ተከታታይ በሆነ ሰባት ሌሊቶችና ስምንት ቀናቶች ውስጥ በእነርሱ ላይ ለቀቃት። ህዝቦችንም፤ በውስጧ የተጣሉ ሆነው ልክ ክፍት እንደሆኑ የዘንባባ ግንዶች ታያቸዋለህ። ከእነርሱ መካከል ቀሪን ታያለህን?

* በጥመታቸው ምክኒያት ተጠፉ ለማለትም ያመቻል።

وَجَآءَ فِرۡعَوۡنُ وَمَن قَبۡلَهُۥ وَٱلۡمُؤۡتَفِكَٰتُ بِٱلۡخَاطِئَةِ ﴿٩﴾ فَعَصَوۡاْ رَسُولَ رَبِّهِمۡ فَأَخَذَهُمۡ أَخۡذَةٗ رَّابِيَةً ﴿١٠﴾

**9-10.** ፈርዖን፤ ከበፊቱ የነበሩትን ሰዎች፤ ተገልባጮችም (የሉጥ ሰዎች ከተሞች) ኃጢአትን ፈፀሙ፡፡ የጌታቸውንም መልዕክተኛ ትዕዛዝ ጣሱ፤ የበረታችንም ቅጣት ቀጣቸው፡፡

إِنَّا لَمَّا طَغَا ٱلۡمَآءُ حَمَلۡنَٰكُمۡ فِي ٱلۡجَارِيَةِ ﴿١١﴾ لِنَجۡعَلَهَا لَكُمۡ تَذۡكِرَةٗ وَتَعِيَهَآ أُذُنٞ وَٰعِيَةٞ ﴿١٢﴾

**11-12.** እኛ ውሃው ባየለ ጊዜ በተንሳፋፊይቱ ታንኳ ውስጥ ጫንናችሁ፡፡ (ይህንም ያደረግነው) ለእናንተ መገሰጫ ልናደርጋትና አጥኚ የሆነችም ጆሮ ታጠናት ዘንድ ነው፡፡

فَإِذَا نُفِخَ فِي ٱلصُّورِ نَفۡخَةٞ وَٰحِدَةٞ ﴿١٣﴾ وَحُمِلَتِ ٱلۡأَرۡضُ وَٱلۡجِبَالُ فَدُكَّتَا دَكَّةٗ وَٰحِدَةٗ ﴿١٤﴾ فَيَوۡمَئِذٖ وَقَعَتِ ٱلۡوَاقِعَةُ ﴿١٥﴾

**13-15.** በቀንዱ አንዲት መነፋት በተነፋች ጊዜ፡፡ ምድርና ጋራዎች (ከየስፍራቸው) በተነሱና አንዲትን መሰባበር በተሰባበሩ (አንዲትን መዘርጋት በተዘረጋች) ጊዜ፡፡ በዚያ ቀን ኋኝቱ ትሆናለች (ትንሳኤ) ትከሰታለች፡፡

وَٱنشَقَّتِ ٱلسَّمَآءُ فَهِيَ يَوۡمَئِذٖ وَاهِيَةٞ ﴿١٦﴾ وَٱلۡمَلَكُ عَلَىٰٓ أَرۡجَآئِهَاۚ وَيَحۡمِلُ عَرۡشَ رَبِّكَ فَوۡقَهُمۡ يَوۡمَئِذٖ ثَمَٰنِيَةٞ ﴿١٧﴾ يَوۡمَئِذٖ تُعۡرَضُونَ لَا تَخۡفَىٰ مِنكُمۡ خَافِيَةٞ ﴿١٨﴾

**16-18.** ሰማይም ትቀደዳለች፡፡ ስለዚህ እርሷ በዚያ ቀን ደካማ ናት፤ መላዕክትም በየጫፎቿ ላይ ይሆናሉ፡፡ የጌታህንም ዓርሽ በዚያ ቀን ስምንት መላዕክት* ከበላያቸው ይሸከማሉ፡፡ በዚያ ቀን ከናንተ ተደባቂ (ነገሮች) የማይደበቁ ሲሆኑ ትቅቀረባላችሁ፡፡

* ስምንት ሰልፍ ማለትም ሊሆን እንደሚችል የፈሰሩ አሉ፡፡

فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ فَيَقُولُ هَآؤُمُ ٱقۡرَءُواْ كِتَٰبِيَهۡ ﴿١٩﴾ إِنِّي ظَنَنتُ أَنِّي مُلَٰقٍ حِسَابِيَهۡ ﴿٢٠﴾ فَهُوَ فِي عِيشَةٖ رَّاضِيَةٖ ﴿٢١﴾ فِي جَنَّةٍ عَالِيَةٖ ﴿٢٢﴾ قُطُوفُهَا دَانِيَةٞ ﴿٢٣﴾ كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ هَنِيٓـَٔۢا بِمَآ أَسۡلَفۡتُمۡ فِي ٱلۡأَيَّامِ ٱلۡخَالِيَةِ ﴿٢٤﴾

**19-24.** ያ መጽሀፉን በቀኝ እጁ የተሰጠ ሰውማ ለጓደኞቹ፡- እንኩ መጽሐፌን እንብቡ ይላል። እኔ ምርመራየን የምገናኝ መሆኔን አረጋገጥኩ። እርሱም በተወደደች ኑሮ ውስጥ ይሆናል። በከፍተኛይቱ ገነት ውስጥ። ፍሬዎቿ ቅርቦች የሆኑ። በአለፉት ቀናት ውስጥ (በምድረ ዓለም) ባስቀደማችሁት ምክንያት ብሉ፤ ጠጡም ይባላሉ።

وَأَمَّا مَنْ أُوتِيَ كِتَـٰبَهُۥ بِشِمَالِهِۦ فَيَقُولُ يَـٰلَيْتَنِي لَمْ أُوتَ كِتَـٰبِيَهْ ﴿٢٥﴾ وَلَمْ أَدْرِ مَا حِسَابِيَهْ ﴿٢٦﴾
يَـٰلَيْتَهَا كَانَتِ ٱلْقَاضِيَةَ ﴿٢٧﴾ مَآ أَغْنَىٰ عَنِّي مَالِيَهْ ۜ ﴿٢٨﴾ هَلَكَ عَنِّي سُلْطَـٰنِيَهْ ﴿٢٩﴾ خُذُوهُ
فَغُلُّوهُ ﴿٣٠﴾ ثُمَّ ٱلْجَحِيمَ صَلُّوهُ ﴿٣١﴾ ثُمَّ فِي سِلْسِلَةٍ ذَرْعُهَا سَبْعُونَ ذِرَاعًا فَٱسْلُكُوهُ ﴿٣٢﴾ إِنَّهُۥ
كَانَ لَا يُؤْمِنُ بِٱللَّهِ ٱلْعَظِيمِ ﴿٣٣﴾ وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلْمِسْكِينِ ﴿٣٤﴾ فَلَيْسَ لَهُ ٱلْيَوْمَ هَـٰهُنَا
حَمِيمٌ ﴿٣٥﴾ وَلَا طَعَامٌ إِلَّا مِنْ غِسْلِينٍ ﴿٣٦﴾ لَّا يَأْكُلُهُۥٓ إِلَّا ٱلْخَـٰطِـُٔونَ ﴿٣٧﴾

**25-37.** ያ መጽሐፉን በግራው የተሰጠ ሰው ደግሞ ዋ ጥፋቴ ምነው መጽሐፌን ባልተሰጠሁ ይላል። ምርመራዬንም ምን እንደሆነ ባላወቅኩ። እርሷ ሞት ምነው የህይወቴ የመጨረሻ ፍፃሜ በሆነች። ገንዘቤ ከእኔ ምንንም አልጠቀመኝም። ኃይሌ (ስልጣኔ) ከእኔ ላይ ጠፋ ይላል። ያዙት ከዚያ እጁን ከአንገቱ ጋር እሰሩት። ከዚያም በእሳት ውስጥ አስገቡት። ከዚም እርዝመቷ ሰባ ክንድ በሆነች ሰንሰለት ውስጥ አስገቡት፤ እርሱ ታላቅ በሆነው አላህ አያምንም ነበርና። ድሆችንም* በማብላት ላይ አያነሳሳም ነበርና። ለእርሱ ዛሬ እዚህ ቦታ ዘመድንም ሆነ ወገን ማንም የለውም። ምግብም ከእሳት ሰዎች ቁስል እጣቢ እዥ በስተቀር የለውም። ይህን ምግብ ኃጢአተኞች እንጂ ሌላ አይበላውም (ይባላል)።

✶ የላሟ ምዕራፍ ላይ (83) ላይ የተቀመጠውን ማብራሪያ ተመልከት። የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አንድ ሰው እንዲህ ሲል ጠየቃቸው። «በኢስላም ውስጥ ከመልካም ስራዎች መካከል በላጩ የቱ ነው?» እሳቸውም«ድሆችን መመገብና ለምታውቀውም ሆነ ለማታውቀው ሰው ሰላምታ መስጠት ነው» ብለው መለሱለት።»

فَلَآ أُقْسِمُ بِمَا تُبْصِرُونَ ﴿٣٨﴾ وَمَا لَا تُبْصِرُونَ ﴿٣٩﴾ إِنَّهُۥ لَقَوْلُ رَسُولٍ كَرِيمٍ ﴿٤٠﴾
وَمَا هُوَ بِقَوْلِ شَاعِرٍ ۚ قَلِيلًا مَّا تُؤْمِنُونَ ﴿٤١﴾ وَلَا بِقَوْلِ كَاهِنٍ ۚ قَلِيلًا مَّا تَذَكَّرُونَ ﴿٤٢﴾
تَنزِيلٌ مِّن رَّبِّ ٱلْعَـٰلَمِينَ ﴿٤٣﴾

38-43. በምታዩትም ሆነ በማታዩት ነገር ሁሉ እምላለሁ*1። ቁርኣን የተከበረው መልዕክተኛ (ጂብሪል) ቃል ነው።*2 እርሱም የባለ ቅኔ ቃል ግጥም አይደለም። ጥቂትን ብቻ ታምናላችሁ። የጠንቋይም ቃል አይደለም። ጥቂትን ብቻ ታስታውሳላችሁ። ከዓለማት ጌታ የተወረደ ነው።

*1 አልምልም ማለት ሊሆንም ይችላል።

*2 ይህ አባባል ያነበበው ነቢዩ ሙሐመድ ናቸው ወይም መላኩ ጂብሪል ነው ለማለት እንጂ የአላህ ቃል አለመሆኑን አያመለክትም። መስሏቸው ቁርኣን የአላህ ቃል አይደለም ብለው ህዝብን የሚያሳስቱ ብዙ አሉና ተጠንቀቋቸው።

وَلَوْ تَقَوَّلَ عَلَيْنَا بَعْضَ ٱلْأَقَاوِيلِ ﴿٤٤﴾ لَأَخَذْنَا مِنْهُ بِٱلْيَمِينِ ﴿٤٥﴾
ثُمَّ لَقَطَعْنَا مِنْهُ ٱلْوَتِينَ ﴿٤٦﴾ فَمَا مِنكُم مِّنْ أَحَدٍ عَنْهُ حَٰجِزِينَ ﴿٤٧﴾

44-47. በእኛ ላይም ከፊልን ቃላት እንኳን (ያላልነው) በቀጠፈ ኖሮ፤ በኃይል በቀጣነው ነበር። ከዚያ ከእርሱ የልቡን ስር የተንጠላጠለበትን (ጅማት) በቆረጥን ነበር። ከናንተም ውስጥ ከእርሱ ላይ ከልካዮች ምንም አይኖሩም።

وَإِنَّهُۥ لَتَذْكِرَةٌ لِّلْمُتَّقِينَ ﴿٤٨﴾ وَإِنَّا لَنَعْلَمُ أَنَّ مِنكُم مُّكَذِّبِينَ ﴿٤٩﴾ وَإِنَّهُۥ لَحَسْرَةٌ عَلَى
ٱلْكَٰفِرِينَ ﴿٥٠﴾ وَإِنَّهُۥ لَحَقُّ ٱلْيَقِينِ ﴿٥١﴾ فَسَبِّحْ بِٱسْمِ رَبِّكَ ٱلْعَظِيمِ ﴿٥٢﴾

48-52. እርሱ (ቁርኣን) ለጥንቅቆቹ ብቻ መገሰጫ ነው። እኛም ከናንተ ውስጥ አስተባባዮች መኖራቸውን በእርግጥ እናውቃለን። እርሱ (ቁርኣንም) በከሓዲያን ላይ ፀፀት ነው። እርሱም የተረጋገጠ እውነት ነው። እናም የታላቁን ጌታህን ስም (ታላቁን ጌታህን) አጥራው።

**ከአረጋጋጭቱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-52) ከምናገኛቸው አንኳርነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
2. እነኚህ ህዝቦች ሙቶ መነሳትን ያምኑ እንዳልነበር፤
3. ነብዩ (ﷺ) ማስከፋትና ትዕዛዛቸውን መንቀፍ ለሁለቱም ዓለም ከስረት ዋና ምክንያት መሆኑን፤
4. ከመአበሉ ታሪክ ብዙ መማር እንዳለብን፤
5. ቁርኣን ያለ ምንም ጥርጣሬ የአላህ ቃል መሆኑን፤
6. ሙቶ መነሳትን እውነት ብሎ ማመንና ማረጋገጥ፤
7. ይህች ዓለም አብቅታ ሁለተኛው ዓለም እንዴት እንደሚጀመር በግልፅ ማሳየት፤
8. የቂያማ ቀንና የሚያስከትለው መጥፎነት፤
9. በአላህ ፊት ለሂሳብ መቅረብ እንዳለ መግለፅ፤
10. በመጨረሻ ቀን ማመንን አስፈላጊነት መግለፅ፤

11. በትንሳኤ ዕለት ሰዎች የመልካም ባለቤቶች እና የመጥፎ ተግባር ባለቤቶች ተብለው ተብለው እንደሚከፋፈሉ፤
12. አማኞች የሚያስደስት ነገሮችን ሁሉ ሲያገኙ ከሓዲያን ደግሞ የሚያጋጥማቸው ሁሉ አስከፊና አሰቃቂ መሆኑን፤
13. የሙቶ መነሳት እውነትነት አስፈላጊነት ማረጋገጥ፤
14. ገንዘብ፤ ስልጣን፤ ዘመድና ወዳጅ የሰው ልጅን ከምንም ሊከለክሉት እንደማይችሉ፤
15. ዘካንም ሆነ ሌላን ገንዘብ ነክ ሀቆችን በአግባቡ አለመወጣት ከፍተኛ ወንጀል ስለ መሆኑ፤
16. አላህ በፈለገው መማል እንደሚችል፤ ፍጡራን ግን ያለ አላህ በማንም መማል እንደማይችሉ፤
17. ወህይን፤ ነብይነትን ማረጋገጥና ነብዩ (ﷺ) ዘፋኝ እንዳልሆኑ ቁርኣንም ዘፈን እንዳልሆነ ማረጋገጥ፤
18. ነብዩም (ﷺ) በአላህ ላይ መዋሸት እንደማይችሉ፤
19. ቁርኣን ከአላህ የወረደ ለፈረሃያን ማስታወሺያ፤ ለከሓዲያን መፀፀቻ መሆኑን፤
20. አላህን ሁልጊዜ ከሓዲያን ከሚገልፁበት ማፅዳት ተገቢ መሆኑን እንማራለን፡፡

በአላህ ፈቃድ የአረጋጋጭቱ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ፡፡

## ምዕራፍ (70)
## የመሰላሎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልመዓሪጅ)

سُورَةُ المَعَارِج

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (44) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

سَأَلَ سَآئِلُۢ بِعَذَابٖ وَاقِعٖ ١ لِّلۡكَٰفِرِينَ لَيۡسَ لَهُۥ دَافِعٞ ٢ مِّنَ ٱللَّهِ ذِي ٱلۡمَعَارِجِ ٣
تَعۡرُجُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ إِلَيۡهِ فِي يَوۡمٖ كَانَ مِقۡدَارُهُۥ خَمۡسِينَ أَلۡفَ سَنَةٖ ٤

**1-4.** ወዳቂ (ተከሳች) ከሆነው ቅጣት ጠያቂ ጠየቀ። ከሓዲያን ላይ (ወዳቂ ከሆነው)። ለእርሱ መላሽ የለውም። የ (ሰማያት) መሰላሎች ባለቤት ከሆነው አላህ (መላሽ የለውም)። መላዕክትና መንፈሱም ልኩ ሀምሳ ሺህ ዓመት በሆነ ቀን ውስጥ ወደ እርሱ ያርጋሉ (ይወጣሉ)።

ከመሰላሎች ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነድር ቢን አልሀሪስ፡- ጌታዬ ሆይ! ይህ ቁርኣን የሚለው ነገር ሁሉ ከአንተ ዘንድ የተወረደ እውነት እንደ ሆነ በእኛ ላይ ከሰማይ ድንጋዮች አዝንብብን ወይም አሳማሚ ቅጣት አምጣብን ባለ ጊዜ ነው የወረደው። ያን የለመነውንም ነገር በበድር እለት ወርዶለት ቀምሶታል። ምክንያቱም ከተማረኩና በልዩ የነቢዩ ትዕዛዝ የተገደሉት አሱና ዑቅበህ ናቸው።

فَٱصۡبِرۡ صَبۡرٗا جَمِيلًا ٥ إِنَّهُمۡ يَرَوۡنَهُۥ بَعِيدٗا ٦ وَنَرَىٰهُ قَرِيبٗا ٧

**5-7.** መልካምን ትዕግስት ታገስ። እነርሱ ያንን ቀን ሩቅ አድርገው ያዩታል። እኛም ቅርብ ሆኖ እናየዋለን።

يَوۡمَ تَكُونُ ٱلسَّمَآءُ كَٱلۡمُهۡلِ ٨ وَتَكُونُ ٱلۡجِبَالُ كَٱلۡعِهۡنِ ٩ وَلَا يَسۡـَٔلُ حَمِيمٌ
حَمِيمٗا ١٠ يُبَصَّرُونَهُمۡۚ يَوَدُّ ٱلۡمُجۡرِمُ لَوۡ يَفۡتَدِي مِنۡ عَذَابِ يَوۡمِئِذِۭ بِبَنِيهِ ١١ وَصَٰحِبَتِهِۦ
وَأَخِيهِ ١٢ وَفَصِيلَتِهِ ٱلَّتِي تُـٔۡوِيهِ ١٣ وَمَن فِي ٱلۡأَرۡضِ جَمِيعٗا ثُمَّ يُنجِيهِ ١٤

**8-14.** ሰማይ እንደ ዘይት አተላ በምትሆንበት ቀን። ጋራዎችም በተለያዩ ቀለማት እንደ ተነከረ ሱፍ (ንፋስ) እንደበተነውና እንደሚያበረው በሚሆንበት ቀን። ዘመድም ዘመድን በማይጠይቅበት ቀን (መላሽ የለውም)። (ዘመዶቻቸውን) ያዩዋቸዋል፤ አመፀኛው ከዚያ ቀን ስቃይ (ነፍሱን) በልጆቹ ቤዛ ሊያደርግ ይመኛል። በሚስቱም በወንድሙም፤ በዚያችም በምታስጠጋው ጎሳው። በምድርም ላይ ባለው ሁሉ (ሊበዠ) ከዚያ ሊያድነው (ይመኛል)።

كَلَّآۖ إِنَّهَا لَظَىٰ ﴿١٥﴾ نَزَّاعَةً لِّلشَّوَىٰ ﴿١٦﴾ تَدۡعُواْ مَنۡ أَدۡبَرَ وَتَوَلَّىٰ ﴿١٧﴾ وَجَمَعَ فَأَوۡعَىٰٓ ﴿١٨﴾

**15-18.** ይተው፤ እርሷ (እሳቲቱ) ለዟ ነዲድ እሳት ናት። የራስን ቅል ቆዳ የምትሞሽልቅ ስትሆን፤ (ከእምነት) የዞረንና የሸሸን ሰው (ወደ እርሷ) ትጠራለች። ገንዘብን የሰበሰበንና ዘካውን ሳይሰጥ የቆጠረንም (ትጠራለች)።

۞إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ خُلِقَ هَلُوعًا ﴿١٩﴾ إِذَا مَسَّهُ ٱلشَّرُّ جَزُوعٗا ﴿٢٠﴾ وَإِذَا مَسَّهُ ٱلۡخَيۡرُ مَنُوعًا ﴿٢١﴾
إِلَّا ٱلۡمُصَلِّينَ ﴿٢٢﴾ ٱلَّذِينَ هُمۡ عَلَىٰ صَلَاتِهِمۡ دَآئِمُونَ ﴿٢٣﴾ وَٱلَّذِينَ فِيٓ أَمۡوَٰلِهِمۡ حَقّٞ مَّعۡلُومٞ ﴿٢٤﴾
لِّلسَّآئِلِ وَٱلۡمَحۡرُومِ ﴿٢٥﴾ وَٱلَّذِينَ يُصَدِّقُونَ بِيَوۡمِ ٱلدِّينِ ﴿٢٦﴾ وَٱلَّذِينَ هُم مِّنۡ عَذَابِ رَبِّهِم
مُّشۡفِقُونَ ﴿٢٧﴾ إِنَّ عَذَابَ رَبِّهِمۡ غَيۡرُ مَأۡمُونٖ ﴿٢٨﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِفُرُوجِهِمۡ حَٰفِظُونَ ﴿٢٩﴾ إِلَّا عَلَىٰٓ
أَزۡوَٰجِهِمۡ أَوۡ مَا مَلَكَتۡ أَيۡمَٰنُهُمۡ فَإِنَّهُمۡ غَيۡرُ مَلُومِينَ ﴿٣٠﴾ فَمَنِ ٱبۡتَغَىٰ وَرَآءَ ذَٰلِكَ فَأُوْلَٰٓئِكَ
هُمُ ٱلۡعَادُونَ ﴿٣١﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ لِأَمَٰنَٰتِهِمۡ وَعَهۡدِهِمۡ رَٰعُونَ ﴿٣٢﴾ وَٱلَّذِينَ هُم بِشَهَٰدَٰتِهِمۡ
قَآئِمُونَ ﴿٣٣﴾ وَٱلَّذِينَ هُمۡ عَلَىٰ صَلَاتِهِمۡ يُحَافِظُونَ ﴿٣٤﴾ أُوْلَٰٓئِكَ فِي جَنَّٰتٖ مُّكۡرَمُونَ ﴿٣٥﴾

**19-35.** ሰው ቅጠ ቢስ ሆኖ ተፈጠረ። ክፉ ነገር ባገኘው ጊዜ ብስጭተኛ፤ መልካምም ነገር (ድሎት) ባገኘው ጊዜ ከልካይ ሆኖ ተፈጠረ። ሰጋጆች ብቻ ሲቀሩ። እነዚያ እነርሱ በስግደታቸው ላይ ዘወታሪዎች የሆኑት። እነዚያም በገንዘቦቻቸው ላይ የታወቀ መብት ያላቸው የሆኑት፤ ለለማኝ እና ከልመና ለሚቆጠብም መብት (ያላቸው የሆኑ)፤ እነዚም በፍርዱ ቀን እውነት የሚሉት የሚያረጋግጡ። እነዚያም እነርሱ ከጌታቸው ቅጣት ፈሪዎች የሆኑት። የጌታቸው ቅጣት መምጣቱም ሆን አለመምጣቱ የማያስተማምን ነውና። እነዚያም እነርሱ ብልቶቻቸውን ጠባቂዎች የሆኑት፤*1 በሚስቶቻቸው ወይም እጆቻቸው በያዙዋቸው ባሮች ላይ ሲቀር። እነርሱ በነዚህ የማይወቀሱ ናቸውና። ከዚያ ወዲያ የፈለገ ሰው እነዚያ እነርሱ ድንበር*2 አላፊዎች

ናቸው። እነዚያም እነርሱ አደራዎቻቸውና ቃል ኪዳናቸውን ጠባቂዎች የሆኑት። እነዚያም እነርሱ በምስክሮቻቸው ላይ ቀጥ ያሉት። እነዚያም እነርሱ በሶላቶቻቸው ላይ የሚጠባበቁት። እነዚያ ከዚህ በላይ የተወሱት ሁሉ በገነቶች ውስጥ የሚከበሩ ናቸው።

✷1 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም ሰው በሁለቱ መንገጭላዎቹና በሁለት እግሮቹ መካከል ያሉትን ለመጠበቅ ዋስትና ከሰጠኝ እኔ ጀነትን ዋስትና እሆንለታለሁ»

✷2 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላፉት የሰማሁትን ሐዲስ አስተላፍላችኋለሁ ይህንንም ከኔ ሌላ ማንም አይነግራችሁም። የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ፡- «ከመጨረሻው ቀን መቃረቢያ ምልክቶች መካከል ዕውቀት ይነሳል። መሃይምነት ይንሰራፋል፤ ዝሙት ይበዛል። አስካሪ መጠጥ በአደባባይ ይጠጣል። የወንዶች ቁጥር ይቀንሳል። ሴቶች ቁጥር አንድ ወንድ ለሃምሳ ሴቶች አስተዳዳሪ እስኪሆን ድረስ ይበዛል።»

فَمَالِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ قِبَلَكَ مُهۡطِعِينَ ﴿٣٦﴾ عَنِ ٱلۡيَمِينِ وَعَنِ ٱلشِّمَالِ عِزِينَ ﴿٣٧﴾
أَيَطۡمَعُ كُلُّ ٱمۡرِيٕٖ مِّنۡهُمۡ أَن يُدۡخَلَ جَنَّةَ نَعِيمٖ ﴿٣٨﴾

**36-38.** እነዚያ በአላህ የካዱት ወደ አንተ በኩል አንገቶቻቸውን መዝዘው የሚያተኩሩት ምን አላቸው? ከቀኝና ከግራ ክፍልፍል ጭፍሮች ሲሆኑ፤ ከእነርሱ እያንዳንዱ ሰው የፀጋይቱን ገነት መግባትን ይከጅላልን?

كَلَّآۖ إِنَّا خَلَقۡنَٰهُم مِّمَّا يَعۡلَمُونَ ﴿٣٩﴾ فَلَآ أُقۡسِمُ بِرَبِّ ٱلۡمَشَٰرِقِ وَٱلۡمَغَٰرِبِ إِنَّا لَقَٰدِرُونَ ﴿٤٠﴾
عَلَىٰٓ أَن نُّبَدِّلَ خَيۡرٗا مِّنۡهُمۡ وَمَا نَحۡنُ بِمَسۡبُوقِينَ ﴿٤١﴾

**39-41.** ይከልከል፤ በፍፁም እኛ ከሚያውቁት ነገር ከፍቶት ጠብታ ፈጠርናቸው። (እናም ጉዳዩ ከሓዲያን እንደሚሉት አይደለም)። በምስራቆችና በምዕራቦች ጌታ እምላለሁ፤ እኛ በእርግጥ ቻዮች ነን። ከእነርሱ የተሻለን በመለወጥ ላይ እኛም ተሸናፊዎች አይደለንም።

ከመሰላሎች ምዕራፍ ከ (38-39) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ከሓዲያን በነብዩ (ﷺ) ዙሪያ እየተሰባሰቡ የሚሉትን ይሰሙ፤ ያስተባብሉ ያፌዙ ስለነበር ብሎም ለሙስሊሞች፡- እነኚህ ጀነት ከገቡማ እኛም በይበልጥ ጀነት እንገባለን ይሉ ስለነበር ነው። (ዋሒዲ)

فَذَرۡهُمۡ يَخُوضُواْ وَيَلۡعَبُواْ حَتَّىٰ يُلَٰقُواْ يَوۡمَهُمُ ٱلَّذِي يُوعَدُونَ ﴿٤٢﴾ يَوۡمَ يَخۡرُجُونَ مِنَ
ٱلۡأَجۡدَاثِ سِرَاعٗا كَأَنَّهُمۡ إِلَىٰ نُصُبٖ يُوفِضُونَ ﴿٤٣﴾ خَٰشِعَةً أَبۡصَٰرُهُمۡ تَرۡهَقُهُمۡ ذِلَّةٞۚ ذَٰلِكَ
ٱلۡيَوۡمُ ٱلَّذِي كَانُواْ يُوعَدُونَ ﴿٤٤﴾

**42-44.** ያንንም የሚስፈራሩበትን ቀናቸውን እስከሚያገኙ ድረስ ተዋቸው፤ በአሉ ቧልታዎች ዉስጥ ይዋኙ። ይጨዋቱም። ያ ቀን ወደ ጣዖት እንደሚሽቀዳደሙ ሆነው ከመቃብሮቻቸው ፈጥነው የሚወጡበትን ቀን እስከሚገናኙ ድረስ ተዋቸው። ዓይኖቻቸው ያፈሩ ሆነው፤ ውርደት ትሸፍናቸዋለች። ይህ ቀን ያ ይስፈራሩበት የነበሩት ቀን ነው።

### ከመሰላሎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-44) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. የአላህ ቅጣት እንዲመጣ መለመን ክልክል መሆኑን፤
2. ለሁሉም ነገር ትዕግስት አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
3. የሙቶ መነሳት ነገር ምንም ጥርጣሬ ሊገባው እንዳማይችል፤
4. የቂያማ ሁኔታ አሳሳቢ ስለመሆኑና ዘመድ ለዝማድ እንኳን የማይጠያየቅበት ቀን መሆኑን፤
5. የአላህን ዒባዳ አለመተግበር ሊያስከትለው የሚችለው አደጋ ምን እንደሚመስል ;
6. ከሰዎች ፀያፍ ባህሪያት መካከል አስከፊው ባህሪያት ስግግብነት መሆኑን፤
7. የዚህን አስከፊ በሽታ መድህኒት ምን እንደሆነ መጠቆም፤
8. እሱም ስንት ነገሮች መሆናቸውን መግለፅ መሆኑን፤
9. በዚህ አንቀፅ የተጠቀሱትን ትዕዛዛት መተግበርና እርም ከሆኑ ነገሮችም መቆጠብ መሆኑን፤
10. ስለ ዝሙት አስከፊነት ማስተማር፤
11. ስለ አማና ክብደት ማስተማር፤
12. ስለ ምስክርነት ከፍተኛ ኃላፊነት መሆን ማስተማር፤
13. የሶላትን ክብደት እንዲሁ በአጭሩ እንማራለን።
14. ነብዩ (ﷺ) በመካ ሳሉ የነበሩበትን ሁኔታ መግለፅ፤
15. የሰው ልጅ ለጀነት የሚበቃው በስራው እንጂ አመጣጡማ ከአደም፤ ከሐዋ እና ከኢሳ በስተቀር ከደካማ ፈሳሽ እንደሆነ፤
16. ስለ መጀመሪያ አፈጣጠራችን ማወቅ ለሁለተኛው ዓለም መኖር ማስረጃ እንደሚሆን፤
17. ሙቶ መነሳት ያለማመንታት መቀበል እንዳለብን ማሳየት፤
18. ክህደት ሰዎች ኑሮ ላይ ላዩን ሲታይ ያማረና የሰመረ ቢመስልም ውስጡ የሚኮሰኩስና ውስብስብ መሆኑን፤
19. የነብይነት ግዴታ መልዕክት ከማድረስ ያለፈ እንዳልሆነ፤
20. የትንሳኤ ዕለት ሰዎች ከቀብሮቻቸው እየተሯሯጡ እንደሚወጡና ለዚህ ቀን ቀደም ብሎ መዘጋጀቱ አስፈላጊ መሆኑን፤
21. ስለ አማና ክብደት፤ የነብዩ (ﷺ) በመካ ሳሉ የነበሩበት ሁኔታ መግለፁ እንማራለን።

**በአላህ ፈቃድ የመሰላሎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።**

## ምዕራፍ (71)
## የነብዩ ኑህ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ኑህ)

سُورَةُ نُوحٍ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (28) ናቸው።**
**የሱረቱ ኑህ መግቢያ**

ይህን ስያሜ በብዙሃን የተፍሲር ምሁራን ዘንድ ያገኜ ሲሆን ቡኻሪ ሱረቱ ኢና አርሰልና ብሎታል። የዋና አስተምሮቱን በተመለከተ ለመኮች የኑህን ሰዎች በምሳሌነት መጥቀስ ና ነብዮን በነብዮ ኑህ መመሰል ነው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِنَّآ أَرۡسَلۡنَا نُوحًا إِلَىٰ قَوۡمِهِۦٓ أَنۡ أَنذِرۡ قَوۡمَكَ مِن قَبۡلِ أَن يَأۡتِيَهُمۡ عَذَابٌ أَلِيمٞ ١

1. እኛ ኑህን ህዝቦችህን አሳማሚ ቅጣት ሳይመጣባቸው በፊት አስጠንቅቅ በማለት ወደ ወገኖቹ ላክነው።

قَالَ يَٰقَوۡمِ إِنِّي لَكُمۡ نَذِيرٞ مُّبِينٌ ٢ أَنِ ٱعۡبُدُواْ ٱللَّهَ وَٱتَّقُوهُ وَأَطِيعُونِ ٣
يَغۡفِرۡ لَكُم مِّن ذُنُوبِكُمۡ وَيُؤَخِّرۡكُمۡ إِلَىٰٓ أَجَلٖ مُّسَمًّىۚ إِنَّ أَجَلَ ٱللَّهِ إِذَا جَآءَ لَا يُؤَخَّرُۚ
لَوۡ كُنتُمۡ تَعۡلَمُونَ ٤

2-4. እርሱም አለ፡- ህዝቦቼ ሆይ፣ እኔ ለእናንተ (የቸገራችሁን) ገላጭ የሆንኩ አስጠንቃቂ ነኝ። አላህን ተገዙት፡- ፍሩት፤ እኔንም ታዘዙኝ በማለት አስጠንቃቂ ነኝ። ለእናንተ ኃጢአታችሁን ይምራል እስከ ተወሰነ ጊዜም ያቆያችኋል። አላህ የወሰነው ጊዜ በመጣ ወቅት ግን ለአፍታም አይቆይም። በትክክል የምታውቁት ብትሆኑ ኖሮ በታዘዛችሁ ነበር።

قَالَ رَبِّ إِنِّي دَعَوۡتُ قَوۡمِي لَيۡلٗا وَنَهَارٗا ٥ فَلَمۡ يَزِدۡهُمۡ دُعَآءِيٓ إِلَّا فِرَارٗا ٦ وَإِنِّي كُلَّمَا
دَعَوۡتُهُمۡ لِتَغۡفِرَ لَهُمۡ جَعَلُوٓاْ أَصَٰبِعَهُمۡ فِيٓ ءَاذَانِهِمۡ وَٱسۡتَغۡشَوۡاْ ثِيَابَهُمۡ وَأَصَرُّواْ وَٱسۡتَكۡبَرُواْ
ٱسۡتِكۡبَارٗا ٧ ثُمَّ إِنِّي دَعَوۡتُهُمۡ جِهَارٗا ٨ ثُمَّ إِنِّيٓ أَعۡلَنتُ لَهُمۡ وَأَسۡرَرۡتُ لَهُمۡ إِسۡرَارٗا ٩

**5-9.** ስለተቃወሙትም ጌታየ ሆይ፣ እኔ በሌሊትም ሆነ በቀን ህዝቦቼን ጠራሁ። ጥሪየም ይበልጥ መሸሽን እንጂ ሌላ አልጨመረላቸውም። እኔም ለእነርሱ ትምራቸው ዘንድ ወደ እምነት በጠራኋቸው ቁጥር ጣቶቻቸውን በጆሮዎቻቸው ውስጥ አደረጉ። ልብሶቻቸውንም ተከናነቡ። በመጥፎ ስራቸው ላይ ዘወተሩም። ያለ ልክ መኩራትንም ኮሩ። ከዚያም እኔ በግልፅ ጠራኋቸው። ከዚያ እኔ ለእነርሱ ጥሪየን ይፋ አደረኩ። ለእነርሱም መመስጠርን መሰጠርኩ አለ።

فَقُلۡتُ ٱسۡتَغۡفِرُواْ رَبَّكُمۡ إِنَّهُۥ كَانَ غَفَّارٗا ﴿١٠﴾ يُرۡسِلِ ٱلسَّمَآءَ عَلَيۡكُم مِّدۡرَارٗا ﴿١١﴾
وَيُمۡدِدۡكُم بِأَمۡوَٰلٖ وَبَنِينَ وَيَجۡعَل لَّكُمۡ جَنَّٰتٖ وَيَجۡعَل لَّكُمۡ أَنۡهَٰرٗا ﴿١٢﴾

**10-12.** ጌታችሁን ምህረትን ለምኑት። እርሱም በጣም መሀሪ ነውና። በእናንተ ላይ ዝናምን ተከታታይ አድርጎ ይልካል። በገንዘቦችና በልጆች ይለግሳችኋል። ለእናንተ አትክልቶችን ያደርግላችኋል። ለእናተም ወንዞችን ያደርግላችኋል አልኳቸው።

مَّا لَكُمۡ لَا تَرۡجُونَ لِلَّهِ وَقَارٗا ﴿١٣﴾ وَقَدۡ خَلَقَكُمۡ أَطۡوَارًا ﴿١٤﴾ أَلَمۡ تَرَوۡاْ كَيۡفَ خَلَقَ ٱللَّهُ
سَبۡعَ سَمَٰوَٰتٖ طِبَاقٗا ﴿١٥﴾ وَجَعَلَ ٱلۡقَمَرَ فِيهِنَّ نُورٗا وَجَعَلَ ٱلشَّمۡسَ سِرَاجٗا ﴿١٦﴾
وَٱللَّهُ أَنۢبَتَكُم مِّنَ ٱلۡأَرۡضِ نَبَاتٗا ﴿١٧﴾ ثُمَّ يُعِيدُكُمۡ فِيهَا وَيُخۡرِجُكُمۡ إِخۡرَاجٗا ﴿١٨﴾
وَٱللَّهُ جَعَلَ لَكُمُ ٱلۡأَرۡضَ بِسَاطٗا ﴿١٩﴾ لِّتَسۡلُكُواْ مِنۡهَا سُبُلٗا فِجَاجٗا ﴿٢٠﴾

**13-20.** ለአላህ ተገቢውን ልቅና የማትሰጡበት ምክንያት ለእናንተ ምን አላችሁ? በልዩ ልዩ (በተለያዩ) እርከኖች (ሁኔታዎች) በእርግጥ የፈጠራችሁ ሲሆን። አላህ ሰባት ሰማያት አንዱ ከአንዱ ላይ የተነባበረ ሲሆን እንዴት እንደፈጠረ አታዩምን? በውስጣቸውም ጨረቃን አብሪ አደረገ። ፀሐይንም ብርሃን አደረገ። አላህም ከምድር ማብቀልን አበቀላችሁ።* ከዚያም በውስጧ ይመልሳችኋል። ማውጣትንም ያወጣችኋል። አላህ ምድርን ለእናንተ ምንጣፍ አደረጋት። ከእርሷ ሰፋፊዎችን መንገዶች ትገቡ ዘንድ።

* አባታችን አደምን ከመሬት አፈር በመፍጠርና እኛንም ልጆቹን ከመሬት በሚበቅሉ ነገሮች በመኖራችን ነው። የሰው ልጅ የሚፈጠረው ፍቶትም ከመሬት የሚበቅሉ ውጤቶች ስለሆነ ነው

قَالَ نُوحٌ رَّبِّ إِنَّهُمْ عَصَوْنِي وَٱتَّبَعُواْ مَن لَّمْ يَزِدْهُ مَالُهُۥ وَوَلَدُهُۥٓ إِلَّا خَسَارًا ﴿٢١﴾
وَمَكَرُواْ مَكْرًا كُبَّارًا ﴿٢٢﴾ وَقَالُواْ لَا تَذَرُنَّ ءَالِهَتَكُمْ وَلَا تَذَرُنَّ وَدًّا وَلَا سُوَاعًا
وَلَا يَغُوثَ وَيَعُوقَ وَنَسْرًا ﴿٢٣﴾ وَقَدْ أَضَلُّواْ كَثِيرًاۖ وَلَا تَزِدِ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا ضَلَٰلًا ﴿٢٤﴾

**21-24.** ኑህ አለ፦ ጌታየ ሆይ፣ እነርሱም አመፁብኝ ገንዘቡና ልጁም ከጥፋት በስተቀር ያልጨመረለትን ሰው ተከተሉ። ታላቅንም ተንኮል ያሴሩትን ሰዎች ተከተሉ። መሪዎችም አሉ፦ አማልክቶቻችሁን፤ ወድንም፣ ሱዋዕንም፣ የጉስንም፣ የዑቅንና ነስርን አትተው። በእርግጥ እነዚህን መሪዎች ወይም ጣኦቶች ብዙዎችን ሰዎች አሳሳቱ። ከሓዲያንንም ጥመትን እንጂ ሌላን አትጨምርላቸው አለ።

مِّمَّا خَطِيٓـَٔـٰتِهِمْ أُغْرِقُواْ فَأُدْخِلُواْ نَارًا فَلَمْ يَجِدُواْ لَهُم مِّن دُونِ ٱللَّهِ أَنصَارًا ﴿٢٥﴾

**25.** በኃጢአቶቻቸው ምክንያት ተሰመጡ። እሳትንም እንዲገቡ ተደረጉ። ለእነርሱም ከአላህ ሌላ የሆኑ ረዳቶችን አላገኙም።

وَقَالَ نُوحٌ رَّبِّ لَا تَذَرْ عَلَى ٱلْأَرْضِ مِنَ ٱلْكَٰفِرِينَ دَيَّارًا ﴿٢٦﴾ إِنَّكَ إِن تَذَرْهُمْ يُضِلُّواْ
عِبَادَكَ وَلَا يَلِدُوٓاْ إِلَّا فَاجِرًا كَفَّارًا ﴿٢٧﴾ رَّبِّ ٱغْفِرْ لِي وَلِوَٰلِدَيَّ وَلِمَن دَخَلَ بَيْتِيَ مُؤْمِنًا
وَلِلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتِۖ وَلَا تَزِدِ ٱلظَّٰلِمِينَ إِلَّا تَبَارًۢا ﴿٢٨﴾

**26-28.** ኑህም አለ፦ ጌታየ ሆይ፣ ከከሓዲያን በምድር ላይ (በዓለም ላይ) (እሳቸው በተላኩባት ምድር) የሚኖርን አንድንም ሰው አትተው። አንተ ብትተዋቸው ባሮችህን ያሳስታሉና። ኃጢአተኛ ከሓዲንም እንጂ ሌላን አይወልዱም። ጌታየ ሆይ፣ ለእኔም ለወላጆቼም ትክክለኛ አማኝ ሆኖ በቤቴ ለገባ ሰው ሁሉ ለምዕመናንና ለምዕመናትም ምህረት አድርግ። ከሓዲያንንም ከጥፋት በቀር አትጨምርላቸው አለ።

**ከኑህ ምዕራፍ ከ (1-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከአደም አንስቶ የተላኩት ነብያት የአላህን አንድነት ተውሒድን በሰውች ለማስረፅ የከፈሉትን መስዕዋትነት መጠቆም፤
2. ነብዩ ኑህ ህዝቦቻቸው ባደረሱባቸው ስቃይና ጥሪያቸውን ባስተባበሏቸው ሰዎች ላይ የነበራቸው ትዕግስት፤
3. የሰው ልጅ ከትክክለኛው መንገድ የሚያስሳስተውን ሰው ማንም ይሁን ማን መከተል እንደሌለበት፤

4. አላህን መፍራትና ምህረቱን መለመን ለሀብት መብዛት ዋና ምክንያት እንደሆነ፤
5. በሰው ልጆች አፈጣጠር ሂደት ላይ ያለውን የአላህን ተዐምር በጥሞና መመልከት ግዴታ መሆኑን፤
6. የሁሉም ነብያት አስተምህሮት አላህን ወደ ማምለክ መጥራት በሱ ማጋራትን ማውገዝ እንደነበር፤
7. አላህ የሰው ልጅን ልዩ ክብርን በመስጠት የሚያስብበት አዕምሮ መስጠቱን፤
8. ትክክለኛ አማኞች የነብያትን ፈለግ ተከታዮች ሁሉ በሚያጋጥሟቸው እንቅፋቶች መታገስና በአቋማቸው ፀንተው ትንሽ ሰዎችንም ቢሆን ማስተማር እንዳለባቸው እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ ነቢዩ ኑህ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (72)
## የጋኔን ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልጂን)

سُورَةُ الجِنِّ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (28) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

قُلۡ أُوحِيَ إِلَيَّ أَنَّهُ ٱسۡتَمَعَ نَفَرٞ مِّنَ ٱلۡجِنِّ فَقَالُوٓاْ إِنَّا سَمِعۡنَا قُرۡءَانًا عَجَبٗا ١ يَهۡدِيٓ إِلَى
ٱلرُّشۡدِ فَـَٔامَنَّا بِهِۦۖ وَلَن نُّشۡرِكَ بِرَبِّنَآ أَحَدٗا ٢ وَأَنَّهُۥ تَعَٰلَىٰ جَدُّ رَبِّنَا مَا ٱتَّخَذَ صَٰحِبَةٗ
وَلَا وَلَدٗا ٣ وَأَنَّهُۥ كَانَ يَقُولُ سَفِيهُنَا عَلَى ٱللَّهِ شَطَطٗا ٤ وَأَنَّا ظَنَنَّآ أَن لَّن تَقُولَ
ٱلۡإِنسُ وَٱلۡجِنُّ عَلَى ٱللَّهِ كَذِبٗا ٥

**1-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከአጋንንት የሆኑ ጭፍሮች ቁርኣንን ከእኔ አዳመጡ። ከዚያ እኛ አስደናቂና ወደ ቀጥታ መንገድ የሚመራን ቁርኣን ሰማን በእርሱም አመንን። በጌታችን አንድንም አናጋራም። እነሆ የጌታችን ክብር ላቀ። ሚስትንም ልጅንም አልያዘም። እነሆ ቂላችን በአላህ ላይ ወሰን ያለፈን ውሸት ይናገር ነበር። እኛም ሰዎችና ጋኔኖች በአላህ ላይ ውሸትን ቃል አይናገሩም ማለትን ጠረጠርን አሉ በማለት ወደ እኔ ተወረደ በል።

ከጋኔን ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሰይጣናት የሰማይን ወሬ እያዳመጡ ቆይተው ቁርኣን መውረድ ሲጀምር ተከለከሉ። በዚህ ጊዜ አንዳንድ ነገር ቢኖር ነው ብለው ሲያፈላልጉ ልዩ ልዩ ቡድኖች ተመዳድበው ወደ መካከለኛው ምስራቅ የተላኩት ነብዩ ሱብሒን እየሰገዱ ቁርኣን ሲቀሩ ሰሟቸው። ይህ ነው ያስከለከለን ብለህ የሆነውን ነገሯቸው። ተመልሰው ለዘመዶቻቸው ነገሩ ነብዩ በዚያ ቀን አላያቸውም ነበር አላህ ግን የሆነውን ነገራቸው።

وَأَنَّهُۥ كَانَ رِجَالٞ مِّنَ ٱلۡإِنسِ يَعُوذُونَ بِرِجَالٖ مِّنَ ٱلۡجِنِّ فَزَادُوهُمۡ رَهَقٗا ٦ وَأَنَّهُمۡ ظَنُّواْ
كَمَا ظَنَنتُمۡ أَن لَّن يَبۡعَثَ ٱللَّهُ أَحَدٗا ٧

**6-7.** እነሆ ከሰዎች የሆኑ ወንዶች ከአጋንንት በሆኑ ወንዶች ይጠበቁ ነበር። ኩራትንም (ጥመትን) ጨመሯቸው። እነርሱም አላህ አንድንም አይቀሰቅስም ማለትን እንደጠረጠራችሁ ጠረጠሩ።

وَأَنَّا لَمَسْنَا ٱلسَّمَآءَ فَوَجَدْنَـٰهَا مُلِئَتْ حَرَسًا شَدِيدًا وَشُهُبًا ﴿٨﴾ وَأَنَّا كُنَّا نَقْعُدُ مِنْهَا مَقَـٰعِدَ لِلسَّمْعِ ۖ فَمَن يَسْتَمِعِ ٱلْـَٔانَ يَجِدْ لَهُۥ شِهَابًا رَّصَدًا ﴿٩﴾ وَأَنَّا لَا نَدْرِىٓ أَشَرٌّ أُرِيدَ بِمَن فِى ٱلْأَرْضِ أَمْ أَرَادَ بِهِمْ رَبُّهُمْ رَشَدًا ﴿١٠﴾ وَأَنَّا مِنَّا ٱلصَّـٰلِحُونَ وَمِنَّا دُونَ ذَٰلِكَ ۖ كُنَّا طَرَآئِقَ قِدَدًا ﴿١١﴾ وَأَنَّا ظَنَنَّآ أَن لَّن نُّعْجِزَ ٱللَّهَ فِى ٱلْأَرْضِ وَلَن نُّعْجِزَهُۥ هَرَبًا ﴿١٢﴾ وَأَنَّا لَمَّا سَمِعْنَا ٱلْهُدَىٰٓ ءَامَنَّا بِهِۦ ۖ فَمَن يُؤْمِنۢ بِرَبِّهِۦ فَلَا يَخَافُ بَخْسًا وَلَا رَهَقًا ﴿١٣﴾ وَأَنَّا مِنَّا ٱلْمُسْلِمُونَ وَمِنَّا ٱلْقَـٰسِطُونَ ۖ فَمَنْ أَسْلَمَ فَأُو۟لَـٰٓئِكَ تَحَرَّوْا۟ رَشَدًا ﴿١٤﴾ وَأَمَّا ٱلْقَـٰسِطُونَ فَكَانُوا۟ لِجَهَنَّمَ حَطَبًا ﴿١٥﴾

**8-15.** እኛም ሰማይን ለመድረስ ፈለግን ብርቱ ጠባቂዎችንና ችቦዎችንም ተሞልታ አገኘናት። እኛም ከእርሷ ወሬን ለማዳመጥ በመቀመጫዎች እንቀመጥ ነበር። አሁን ግን የሚያዳምጥ ሁሉ ተጠባባቂ የእሳት ችቦን ያገኛል። እኛም በምድር ውስጥ ባሉ ሰዎች ክፉ ተሽቷል? ወይስ በእነርሱ ጌታቸው ደግን ነገር ሽቷል ማለትን አናውቅም። ከእኛም ውስጥም ደጎች አሉ። ከእኛም ውስጥ ከዚህ ሌላ የሆኑ አሉ። የተለያዩ መንገዶች ባለቤቶች ነበርን። እኛም አላህን በምድር ውስጥ ፈፅሞ የማናቅተው ሸሽተንም ፈፅሞ የማናመልጠው መሆናችንን አረጋገጥን። እኛም መሪውን በሰማን ጊዜ በእርሱ አመንን። ያ፣ በጌታው የሚያምን ሰው ሁሉ መጎደልንም ሆነ መጨመርን አይፈራም። ከእኛም ውስጥ ሙስሊሞች አሉ። ከእኛም ውስጥ በዳዩች አሉ። እነዚያ የሰለሙ ሰዎች ቅንን መንገድ መረጡ። እነዚያ በዳዩችማ ለገሀነም ማገዶ ሆኑ።

وَأَلَّوِ ٱسْتَقَـٰمُوا۟ عَلَى ٱلطَّرِيقَةِ لَأَسْقَيْنَـٰهُم مَّآءً غَدَقًا ﴿١٦﴾ لِّنَفْتِنَهُمْ فِيهِ ۚ وَمَن يُعْرِضْ عَن ذِكْرِ رَبِّهِۦ يَسْلُكْهُ عَذَابًا صَعَدًا ﴿١٧﴾

**16-17.** ሰዎች ሁሉ በአላህ በመንገድ ላይ ቀጥ ባሉ ኖሮ* ልንሞክራቸው ብዙ ዝናብን ባጠጣናቸው ነበር። ያ ጌታውን ከማስታወስ የሚያፈገፍግ ሰው አስቸጋሪ ቅጣት ውስጥ ያስገባዋል።

* አዎ ሰዎች የአላህን ዲን ባከበሩ ጊዜ የኑሮ ጭንቀት አይኖርባቸውም።

وَأَنَّ ٱلْمَسَـٰجِدَ لِلَّهِ فَلَا تَدْعُوا۟ مَعَ ٱللَّهِ أَحَدًا ﴿١٨﴾

**18.** መስጊዶች ሁሉ የአላህ ብቻ ናቸው። እናም በውስጣቸው ከአላህ ጋር አንድንም አትገዙ (ማለትም ተወረደልኝ)።

ከጋኔን (18) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ጋኔን ለነብዩ (ﷺ) ፍቀድልን መስጊድ መጥተን ከእርሰዎ ጋር ጀመዓ እንሰገድ ስለሏቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَأَنَّهُۥ لَمَّا قَامَ عَبۡدُ ٱللَّهِ يَدۡعُوهُ كَادُواْ يَكُونُونَ عَلَيۡهِ لِبَدٗا ١٩

**19.** እነሆ የአላህ ባሪያ (ሙሐመድ) አላህን የሚያጠራው ሆኖ በተነሳ ጊዜ ጋኒኖቹ በእርሱ ላይ ድርብርቦች ሊሆኑ ቀረቡ።

قُلۡ إِنَّمَآ أَدۡعُواْ رَبِّي وَلَآ أُشۡرِكُ بِهِۦٓ أَحَدٗا ٢٠ قُلۡ إِنِّي لَآ أَمۡلِكُ لَكُمۡ ضَرّٗا وَلَا رَشَدٗا ٢١
قُلۡ إِنِّي لَن يُجِيرَنِي مِنَ ٱللَّهِ أَحَدٞ وَلَنۡ أَجِدَ مِن دُونِهِۦ مُلۡتَحَدًا ٢٢ إِلَّا بَلَٰغٗا مِّنَ ٱللَّهِ
وَرِسَٰلَٰتِهِۦۚ وَمَن يَعۡصِ ٱللَّهَ وَرَسُولَهُۥ فَإِنَّ لَهُۥ نَارَ جَهَنَّمَ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدًا ٢٣ حَتَّىٰٓ إِذَا
رَأَوۡاْ مَا يُوعَدُونَ فَسَيَعۡلَمُونَ مَنۡ أَضۡعَفُ نَاصِرٗا وَأَقَلُّ عَدَدٗا ٢٤

**20-24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኔ የማመልከው ጌታየን ብቻ ነው። በእርሱ አንድንም አላጋራም በል። እኔ ለእናንተ ጉዳትንም ሆነ ማቅናትን አልችልም በል። እኔ ከአላህ ቅጣት አንድም አያድነኝም። ከእርሱ ሌላ መጠጊያ አላገኝም በል። ከአላህ የሆኑ መልዕክቶችን ከማድረስ በስተቀር አልችልም። በአላህና በመልዕክተኛው የሚያምፅ ሰው ሁሉ ለእርሱ የገሀነም እሳት አለው። በውስጧም ዘላለም ዘወታሪዎች ሲሆኑ። የሚስፈራሩበትንም ባዩ ጊዜ ረዳተ ደካማ ቁጥሩም አነስተኛ የሆነው ማን እንደሆነ በእርግጥ ያውቃሉ።

ከጋኔን (22) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ የጋኔን መሪ ሙሐመድ አላህ እንዲጠብቀው ነው የሚፈልገው። እኔ ግን ልጠብቀው እችል ነበር ብሎ ስለተናገረ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

قُلۡ إِنۡ أَدۡرِيٓ أَقَرِيبٞ مَّا تُوعَدُونَ أَمۡ يَجۡعَلُ لَهُۥ رَبِّيٓ أَمَدًا ٢٥ عَٰلِمُ ٱلۡغَيۡبِ فَلَا يُظۡهِرُ عَلَىٰ
غَيۡبِهِۦٓ أَحَدًا ٢٦ إِلَّا مَنِ ٱرۡتَضَىٰ مِن رَّسُولٖ فَإِنَّهُۥ يَسۡلُكُ مِنۢ بَيۡنِ يَدَيۡهِ وَمِنۡ خَلۡفِهِۦ
رَصَدٗا ٢٧ لِّيَعۡلَمَ أَن قَدۡ أَبۡلَغُواْ رِسَٰلَٰتِ رَبِّهِمۡ وَأَحَاطَ بِمَا لَدَيۡهِمۡ وَأَحۡصَىٰ كُلَّ شَيۡءٍ عَدَدَۢا ٢٨

**25-28.** ያ! የምትስፈራሩበት ነገር ቅርብ ወይም ጌታየ ለእርሱ የተወሰነ ጊዜን የሚያደርግለት እሩቅ መሆኑን አላውቅም። እርሱም እሩቁን ሚስጢር አዋቂ ነው። በሚስጢሩም ላይ ከመልዕክተኛው ለወደደው ቢሆን እንጂ ለሌላ አንድንም አያሳውቅም። አይገልፅም። ለእርሱም ከበስተፊቱም ከበስተኋላውም ጠባቂዎቸን ያደርግለታል። ከእነርሱ ዘንድ ባለው ነገር እውቀት የከበበና ነገሩንም ሁሉ በቁጥር ያጠቃለለ ሲሆን የጌታቸውን መልዕክቶች ያደረሱ መሆናቸውን ያውቅ (ዘንድ ጠባቂ ያደርጋል)።

**ከጋኔን ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-28) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በአላህ መንገድ ቀጥ ማለት ወደ ጥሩ ነገር እንደሚያደርስ፤
2. ንብረት ፈታኝ መሆኑንና ከገንዘብ ፈተና ነፃ የሚወጣው ትንሽ ሰዎች መሆናቸውን፤
3. ከአላህ ሌላ ማንንም ከችግር ለመዳን መማፀን ክልክል ቢሆንም ከአላህ ሌላ ለሆነ ነገር መስገድ የበለጠ አስከፊ ስለ መሆኑ፤
4. ኸይርም ሆነ ሸር ቅንነትንም ሆነ ጥሜት በአላህ እጅ እንጂ በማንም እጅ እንዳልሆነ፤
5. አላህንና ነብዩን ማስከፋት ለዱንያም ሆነ ለአኼራ ቅጣት ዋና ምክንያት መሆኑን፤
6. የውሃ አስፈላጊነትና አንገብጋቢነት፤
7. ሰዎችም ሆኑ ጋኔኖች የኢስላም ጮራ ለማዳከም ከፍተኛ ሙከራ እንዳደረጉ፤
8. ጥቅምም ሆነ ጉዳት በአላህ እጅ ብቻ እንደሆነ ሌላው ቀርቶ ነብዩ እንኳን ራሳቸውን ለማዳን እንደማይችሉ፤
9. የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ኃላፊነት መልዕክታቸውን ለህዝብ ማድረስ ብቻ እንደነበር፤
10. መስጊዶች የአላህ ቤቶች መሆናቸውን፤
11. ገይብ የተባለ ነገርን ሁሉ ማወቅ ብቸኛ ስልጣን ስለመሆኑ፤
12. ለአንዳንድ ነብያት ወይም መልአክ አንዳንድ ገይቦችን እንደሚሳውቃቸውና ከሰይጣን ተንኮሎች የተጠበቀ መሆኑን፤
13. አላህ እውቀት ሁሉን ያጠቃለለ ስለ መሆኑና ከእሱ የሚሰወር አንድም ነገር አለመኖሩን፤
14. ከአላህ መልዕክተኞች በስተቀር (ገይብን ከአይን የተሰወሩ ነገሮችን) አውቃለሁ የሚሉ ሰዎች ሁሉ አባባላቸው ውድቅ እንደሆነ፤
15. የነብዩ (ﷺ) ነብይነትን ማረጋገጥና የሰውች ብቻ መልዕክተኛ ሳይሆኑ ለጋኔንም መላካቸውን፤
16. የቁርኣንን ትልቅነትና የአላህ ቃልነትን መግለፅ፤
17. ሽርክን አውግዞ ተውሒድን ማረጋገጥና ማሞገስ፤
18. ሰዎች እንደጋኔን ሊዋሹ እንደሚችሉና ይህም መዋሸት እንደማይገባ፤
19. እምነት የሌለው ሰው ቂል ሊባል እንደሚችል፤
20. የብዙ ሰዎች መንገድ መልቀቅ የሚፈጥረው በሚከተሉት አካል ላይ ከንቱ እምነት በማሳደር መሆኑን፤
21. በጋኔን መጠበቅና መታገዝ ክልክል ከመሆኑም በላይ ወደ ሽርክ ሊደርስ እንደሚችል፤
22. ጋኔን የሚባል ፍጡር መኖሩንና ልክ እንደሰው የታዘዙና የተከለከሉ ስለ መሆናቸው፤
23. በመልአክና በጋኔን መካከል ያለውን ግልፅ ግንኙነት መግለፅና ማብራራት፤
24. ከጋኔኖች መካከል በነብዩ (ﷺ) ነብይነት አማኞችና መልካም ሰሪዎች መኖራቸውን፤
25. ልዩነትን በማስፋፋት ስሜትን መከተል ተገቢ አለመሆኑን ማውገዝ፤
26. እውነትን መፈለግ ፍትሀዊነት ምን ያህል አስፈላጊ እንደሆነ መጠቆም፤
27. ጋኔን ነብዩን (ﷺ) ለማዳመጥ የነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት፤
28. ጋኔን ልክ እንደ ሰው ልጅ ብዙ አይነቶች እንደሆኑ፤
29. አላህ ኃያልና ማንም የማመልጠው መሆኑ እንግራለን፤

**በአላህ ፈቃድ የጋኔን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።**

## ምዕራፍ (73)
## የተከናናቢው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሙዘሚል)

سُورَةُ المُزَّمِّلِ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (20) ናቸው።**
**የሱረቱ አል ሙዝዘሚል መግቢያ**

በዚህ ምዕራፍ አስተምህሮት መሰረት በመጀመሪያ ጊዜ ሌሊት መቆም በነብዩ ላይም ሆነ በሌሎች ሙስሊሞች ግዴታ ነበር። ምርጫ የነበራቸው ግማሽ ወይንም ያነሰ ወይንም ከግማሽ የጨመረ በሚል በተጠቀሰው በመጠኑ ብቻ ላይ ነበር። ነብዩም ሆኑ ሌሎች ሙስሊሞች በዚሁ መሰርት መተግበር ጀመሩ። አንዳዱ ልኩን በዉል ባለመረዳታቸው ከተባለው መጠን እንዳያሳንሱ በመፍራት ሙሉ ሌሊት ቁመው ያነጉ ነበር። ይህም ተግባር እየከበዳቸው መጣና እግራቸው ማበጥ ጀመረ። በዚህ ጊዜ ነው አላህ ያሻረላቸውና የመጨረሻዉን አንቀፅ ያወረደላቸው። በሁለቱ መካከል አንደ አመት ያክል ክፍተት ነበር። ኢማሙ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ እናታች ዓኢሻ የዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ከመጀመሪያው ከአመት በኋላ ነው የወረደው ብለዋል። በዚህም መሰረት ግዴታ የነበረው ትርፍ ሶላት ሁኖ ቀጥሏል» ብለዋል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمُزَّمِّلُ ١ قُمِ ٱلَّيۡلَ إِلَّا قَلِيلٗا ٢ نِّصۡفَهُۥٓ أَوِ ٱنقُصۡ مِنۡهُ قَلِيلًا ٣
أَوۡ زِدۡ عَلَيۡهِ وَرَتِّلِ ٱلۡقُرۡءَانَ تَرۡتِيلًا ٤ إِنَّا سَنُلۡقِي عَلَيۡكَ قَوۡلٗا ثَقِيلًا ٥

**1-5.** አንተ ተከናናቢው ሆይ። ሌሊቱን ሁሉ ጥቂት ሲቀር ቁም (ስገድ)። ግማሹን ቁም ወይም ከእርሱ ጥቂትን ቀንስ። ወይም በእርሱ ላይ ጨምር። ቁርኣንንም በዝግታ አንብብ። እኛ በአንተ ላይ ከባድ ቃልን እናወርዳለንና።*

* ቃሉ ቀላል ቢመስልም ተግባሩ ከባድ ነው። አንድ ሰው አንድን በአንድ አፍታ ሊያነብ ይችላል። ተግባሩ ግን እድሜ ልኩን ሳይተገብር ሊሞት ይቿላል።

ከተከናናቢው ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ቁረይሾች ዳር አንነድዋ በተባለው የመሰብሰቢያ አዳራሽ ተሰብስበው ስለ ነብዩ (ﷺ) ምን እንበል በሚል ተወያይተው የደረሱበት አቋም ለነብዩ (ﷺ) ስለደረሳቸውና በልብሳቸው ተሸፋፍነው ሳሉ ነው። (ሱዩጢ)

إِنَّ نَاشِئَةَ ٱلَّيۡلِ هِيَ أَشَدُّ وَطۡـٔٗا وَأَقۡوَمُ قِيلًا ٦ إِنَّ لَكَ فِي ٱلنَّهَارِ سَبۡحٗا طَوِيلٗا ٧
وَٱذۡكُرِ ٱسۡمَ رَبِّكَ وَتَبَتَّلۡ إِلَيۡهِ تَبۡتِيلٗا ٨ رَّبُّ ٱلۡمَشۡرِقِ وَٱلۡمَغۡرِبِ لَآ إِلَٰهَ إِلَّا هُوَ فَٱتَّخِذۡهُ
وَكِيلٗا ٩ وَٱصۡبِرۡ عَلَىٰ مَا يَقُولُونَ وَٱهۡجُرۡهُمۡ هَجۡرٗا جَمِيلٗا ١٠

**6-10.** ሌሊት መነሳት እርሷ (ህዋሳትንና ልብን) ለማስማማት በጣም ብርቱ ናት። ለማንበብም ትክክለኛ ሰዓት ነው። ለአንተ በቀን ውስጥ ረዥም የመዘዋወርያ ሰዓት አለህ። የጌታህን ስም አውሳ። ወደ እርሱም (መገዛት) መቋረጥን ተቋረጥ። (እርሱም) የምስራቅና የምዕራብ ጌታ ነው። ከእርሱ ሌላ ትክክለኛ አምላክ የለም። መጠጊያ አድርገህም ያዘው። ከሓዲያንም በሚሉት ላይ ታገስ። መልካምንም መተው ተዋቸው።

وَذَرۡنِي وَٱلۡمُكَذِّبِينَ أُوْلِي ٱلنَّعۡمَةِ وَمَهِّلۡهُمۡ قَلِيلًا ﴿١١﴾ إِنَّ لَدَيۡنَآ أَنكَالٗا وَجَحِيمٗا ﴿١٢﴾ وَطَعَامٗا ذَا غُصَّةٖ وَعَذَابًا أَلِيمٗا ﴿١٣﴾ يَوۡمَ تَرۡجُفُ ٱلۡأَرۡضُ وَٱلۡجِبَالُ وَكَانَتِ ٱلۡجِبَالُ كَثِيبٗا مَّهِيلًا ﴿١٤﴾

**11-14.** የድሎት ባለቤቶችም ከሆኑት አስተባባዮች ጋር ተወኝ። ጥቂትንም ጊዜ አቆያቸው። ከእኛ ዘንድ ከባድ ማሰሪያዎችና እሳት አሉንና። ጉሮሮን የሚያንቅ ምግብና አሳማሚ ቅጣትም አለ። በዚያ ምድርና ጋራዎች በሚርገፈገፉበት ጋራዎችም ፈሳሽ የአሸዋ ክምር በሚሆኑበት ቀን።

إِنَّآ أَرۡسَلۡنَآ إِلَيۡكُمۡ رَسُولٗا شَٰهِدًا عَلَيۡكُمۡ كَمَآ أَرۡسَلۡنَآ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ رَسُولٗا ﴿١٥﴾ فَعَصَىٰ فِرۡعَوۡنُ ٱلرَّسُولَ فَأَخَذۡنَٰهُ أَخۡذٗا وَبِيلٗا ﴿١٦﴾ فَكَيۡفَ تَتَّقُونَ إِن كَفَرۡتُمۡ يَوۡمٗا يَجۡعَلُ ٱلۡوِلۡدَٰنَ شِيبًا ﴿١٧﴾ ٱلسَّمَآءُ مُنفَطِرُۢ بِهِۦۚ كَانَ وَعۡدُهُۥ مَفۡعُولًا ﴿١٨﴾ إِنَّ هَٰذِهِۦ تَذۡكِرَةٞۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ سَبِيلًا ﴿١٩﴾

**15-19.** (ሰዎች ሆይ!)፣ እኛ ወደ ፈርዖን መልዕክተኛን እንደላክን ሁሉ በእናንተ ላይ መስካሪ መልዕክተኛንም ወደ እናንተ ላክን። ፈርዓውንም መልዕክተኛውን አመፀ። ብርቱ መያዝንም ያዝነው። (የመካ ሰዎች ሆይ)፣ (በአላህ) ብትክዱ ያን ልጆችን ሽበቶዎች የሚያደርገውን ቀን ቅጣት እንዴት ትጠብቃላችሁ። ሰማዩ በዚያ ቀን ተሰንጣቂ ነው። ቀጠሮውም ተፈፃሚ ነው። ይህ መገሰጫ ነው። መዳንንም የሻ (የፈለገ) ሰው ወደ ጌታው የሚያደርሰዉን መንገድ ይይዛል።

۞إِنَّ رَبَّكَ يَعۡلَمُ أَنَّكَ تَقُومُ أَدۡنَىٰ مِن ثُلُثَيِ ٱلَّيۡلِ وَنِصۡفَهُۥ وَثُلُثَهُۥ وَطَآئِفَةٞ مِّنَ ٱلَّذِينَ مَعَكَۚ وَٱللَّهُ يُقَدِّرُ ٱلَّيۡلَ وَٱلنَّهَارَۚ عَلِمَ أَن لَّن تُحۡصُوهُ فَتَابَ عَلَيۡكُمۡۖ فَٱقۡرَءُواْ مَا تَيَسَّرَ مِنَ ٱلۡقُرۡءَانِۚ عَلِمَ أَن سَيَكُونُ مِنكُم مَّرۡضَىٰ وَءَاخَرُونَ يَضۡرِبُونَ فِي ٱلۡأَرۡضِ يَبۡتَغُونَ مِن

فَضْلِ ٱللَّهِ وَءَاخَرُونَ يُقَٰتِلُونَ فِى سَبِيلِ ٱللَّهِ ۖ فَٱقْرَءُوا۟ مَا تَيَسَّرَ مِنْهُ ۚ وَأَقِيمُوا۟ ٱلصَّلَوٰةَ وَءَاتُوا۟
ٱلزَّكَوٰةَ وَأَقْرِضُوا۟ ٱللَّهَ قَرْضًا حَسَنًا ۚ وَمَا تُقَدِّمُوا۟ لِأَنفُسِكُم مِّنْ خَيْرٍ تَجِدُوهُ عِندَ ٱللَّهِ هُوَ
خَيْرًا وَأَعْظَمَ أَجْرًا ۚ وَٱسْتَغْفِرُوا۟ ٱللَّهَ ۖ إِنَّ ٱللَّهَ غَفُورٌ رَّحِيمٌۢ ﴿٢٠﴾

**20.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንተ ከሌሊቱ ሁለት እጅ ያነሰን፤ ግማሹንም ሲሶውንም የምትቆም መሆንህን ጌታህ ያውቃል። (ሙስሊሞች) ከእነዚያም አብረውህ ካሉ ከፊሎች (የሚቆሙ መሆናቸውን ያወቃል)። አላህ ሌሊትና ቀንን ይለካል። ሌሊቱን በሙሉ የማትቆሙት መሆናችሁን አወቀ። እናም በእናንተ ላይ ህጉን ወደ ማቃለል ተመለሰላችሁ። ስለዚህ ከቁርኣን በስግደት የተቻላችሁን ያህል አንብቡ። ከናንተ ውስጥ ሌሎችም በሽተኞች ከአላህ ችሮታ ለመፈለግ በምድር ላይ የሚጓዙ ሌሎችም፤ በአላህ መንገድ ሃይማኖት ላይ የሚጋደሉ እንደሚኖሩ አወቀ። አቃለለላቸውም ከቁርኣን የቻላችሁትን አንብቡ። ሶላትንም ስገዱ። ዘካንም ስጡ። ለአላህ መልካም ብድርንም አበድሩ። ከመልካም ስራም ለነፍሶቻችሁ የምታስቀድሙትን ሁሉ የተሻለና በምንዳም ታላቅ ሆኖ በአላህ ዘንድ ታገኙታላችሁ። አላህን ምህረት ለምኑት። አላህ መህሪና አዛኝ ነውና።

ከተከናናቢው ምዕራፍ (20) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ለነብዩ ባልደረቦችና ለጠቅላላ ሙስሊሞች ሁኔታዎችን ለማግራራት የተወረደ አንቀፅ ነው። ምክንያቱም ሙስሊሞች የምዕራፉን መግቢያ ሲሰሙ በፊት በመቆም እግራቸው እስከሚቆስል ድረስ ለዒባዳ ይታገሉ ነበር።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻ እንዲህ ሲሉ እስተላፈዋል፡- «ነብዩ ሌሊት እግራቸው እስኪሰነጠቅ ድረስ ይቆሙ ነበር። ከዚያም«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ያለፈውም የሚመጣውም ወንጀልህ የተማረልህ ሆኖ እያለ ለምን ይህን ያህል ትቸገራለህ?» በማለት ጠየቅኳቸው። «አመስጋኝ ባሪያ መሆን የለብኝምን?» ሲሉ መለሱልኝ።

ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ሳሊም ኢብኑ ዐብደላህ ኢብኑ ዑመር ኢብኑ አል. ኸጣብ አባታቸውን ዋቢ አድርገው እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል፡- «ዐብደላህ የሌሊት ሶላት የሚሰግድ ቢሆን ኖሮ ያማረ የአላህ አገልጋይ ይሆን ነበር» ሳሊም እንደተናገሩት ዐብደላህ ከዚህ ዕለት በኋላ በሌሊት ጥቂት ካልሆነ በስተቀር አይተኛም ነበር።

1. የሌሊት ሶላት ከቀን ሶላት በምንዳ የበለጠ ሶላት ነው። ነብዩም (ﷺ) ሆኑ ባልደረቦቻቸው ይሰግዱት የነበረው የሌሊት ሶላት በቁርኣን ታዘው ነበር። ይኸው ሶላት ግዴታነቱ ተሽሯል። ሆኖም የሌሊት ሶላት ግዴታ ባይሆንም የተወደደ በመሆኑ ግፊት ማሳደሩ ይመረጣል። ይህም የመልካም ሰዎች ተግባር ነው። እንዲሁም ቁርኣንን ጭር ባለ ሌሊት ብሎም በጥሞና ማንበብ አስፈላጊ ስለመሆኑ ከምዕራፉ ተገልጿል።
2. በየትኛውም መልክ አላህን መዘከር አስፈላጊ ነው። በማንኛውም ጊዜ ጉዳዩን ለማውጣት በአላህ ላይ መመካት ተገቢ ነው። ለሁሉም ነገር የትዕግስት አስፈላጊነት ዋጋው ከፍ ያለ ነው። ነብዩ (ﷺ) ትዕግስት እንዲደርጉ አዘዋል።

3. የነብያትን ሀቀኝነት ማረጋገጥ እምነት መንገድ ሲሆን እነሱን ማስተባበል ለከፋ ቅጣት የሚዳርግ ነው።
4. ሶላትን መስገድና ዘካ መስጠት ግዴታ ነው። ከየትኛውም «ዒባዳ» ዘርፍ ከግዴታው በተጨማሪ መስራት በኢስላም አስፈላጊ ነው። የሰው ልጅ ወንጀል በሰራበት ጊዜ አላህን ምህረት መጠየቁ ግዴታው ሲሆን በሌላ ጊዜ ይህንን ማድረጉ «ሱና» ነው።

ነብዩ (ﷺ) መላኩ ጂብሪል መምጣት እንደጀመረ እየፈሩ ይከናነቡ ስለ ነበር ነው በዚህ አይነት ጥሪ የጠራቸው። እውነትም የኢስላም መልዕክት ከባድ ነው። ትምህርቱም እንዲሁ ከባድ ነው። ኢማሙ ማሊክ «ይህ ከገር ትምህርቶች አንዱ ነው» ሲባሉ «ከቁርአንና ከሃዲስ ትምህርት ቀላል የሚባል የለም» በማለት ከመለሱ በኋላ ያቀረቡት መረጃ ይኸው አንቀፅ ነበር።»

**ከተከናናቢው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-20) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የሌሊት ሶላት ለነብዩ (ﷺ) ግዴታ እንደነበርና ለሙስሊሞችም አስፈላጊነቱን፤
2. ቁርአንን ጭር ባለ ሌሊት ብሎም በጥሞና ማንበብ አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
3. የሌሊት ሶላት ከቀን ሶላት በምንዳ የበለጠ ሶላት መሆኑን፤
4. ስለ ሌሊት ሶላት ግፊት ማሳደር፤
5. በየትኛውም መልክ አላህን መዘከር አስፈላጊ ስለ መሆኑ፤
6. በየትኛውምጉዳይን ለመወጣት በአላህ ላይ መመካት ተገቢ ስለ መሆኑን፤
7. ነብዩም (ﷺ) ትዕግስት እንዲያደርጉ መታዘዛቸውንና አስተባባዮች ስለሚጠብቃቸው ቅጣት፤
8. ለሁሉም ነገር የትዕግስትን አስፈላጊነት፤
9. መልካም ክፍያ ተፈላጊ መሆኑ፤
10. የነብያት ሀቀኝነት አለማረጋገጥና እነሱን ማስተባበል ለከፉ ቅጣት እንደሚዳርግ፤
11. የሙቶ መነሳትን እርግጠኝነት የተለያዩ ሁኔታዎችን በመጥቀስ ማረጋገጥ፤
12. ነብዩም (ﷺ) ሆኑ ባልደረቦቻቸው ይሰግዱት የነበረውን የሌሊት ሶላት ታዘው እንደነበረ፤
13. የሌሊት ሶላት ግዴታነት መሻሩን መጠቆም ብሎም ማብሰር፤
14. ሶላትን መስገድና ዘካን መስጠት ኢስላማዊ ግዴታ ስለመሆኑ፤
15. በየትኛውም ዒባዳ ዘርፍ ከግዴታነት በተጨማሪ መስራት በኢስላም አስፈላጊ ስለመሆኑ፤
16. የሰው ልጅ ወንጀል በሰራበት ጊዜ የአላህን ምህረት መጠየቅ ግዴታ ስለመሆኑና በሌላ ጊዜ ሱና ስለ መሆኑ፤
17. የሰዎች ዋና ዋና ምክንያቶች በሽታ፤ በግል ስራ መወጠር፤ በዳዕዋና በመሰል ስራ መጣበብ መሆናቸውን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የተከናናቢው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (74)
# የልብስ ደራቢው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሙደሲር)

سُورَةُ المُدَّثِّرِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (56) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡمُدَّثِّرُ ١ قُمۡ فَأَنذِرۡ ٢ وَرَبَّكَ فَكَبِّرۡ ٣
وَثِيَابَكَ فَطَهِّرۡ ٤ وَٱلرُّجۡزَ فَٱهۡجُرۡ ٥

**1-5.** አንተ (ልብስ) ደራቢው ሆይ፣*[1] ተነሳና ህዝቦችን አስጠንቅቅ። ጌታህንም አክብር። ልብስህንም አጥራ*[2]። ጣዖትንም ራቅ።

*1 ነብዩ (ﷺ) መልዐኩ ጂብሪል መምጣት እንደጀመረ እየፈሩ ይከናነቡ ስለ ነበር ነው በዚህ አይነት ጥሪ የተጠራው።

ከልብስ ደራቢው ከ (1-5) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- ነብዮ ለአንድ ወር በሒራ ዋሻ አሳልፈው ሲጨርሱ ሸለቆው ውስጥ ሆነው የሆነ ጥሪ ሰሙ ከኋላም ከፊትም ከቀኝም ሆነ ከግራ ሲመለከቱ ማንም አልነበረም። ከዚያም የሁለተኛ ጥሪ ሲሰሙና ወደ ላይ ቀና ሲሉ ጅብሪል በአየር ላይ ሆኖ አዩት። እሱም ሙሐመድ አንተ የአላህ መልዕክተኛ ንህ እኔም ጂብሪል ነኝ አላቸው። ከዚያም ተመልሰው ውሃ አፍሱብኝ ስላሉ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ።)

*2 ጣዉስ የተባሉ ዐሊም ልበስህን አሳጥር ለማለትም ይሆናል ይላሉ።

وَلَا تَمۡنُن تَسۡتَكۡثِرُ ٦ وَلِرَبِّكَ فَٱصۡبِرۡ ٧

**6-7.** ማብዛትንም የምትፈልግ ሆነህ አትለግስ። (ብዙ ዒባዳን ከመስራት አትድከም)። ለጌታህ ትዕዛዝም ታገስ።

فَإِذَا نُقِرَ فِي ٱلنَّاقُورِ ٨ فَذَٰلِكَ يَوۡمَئِذٖ يَوۡمٌ عَسِيرٌ ٩ عَلَى ٱلۡكَٰفِرِينَ غَيۡرُ يَسِيرٖ ١٠

**8-10.** በቀንዱም በተነፋ ጊዜ ነገሩ ሁሉ በዚያ ዕለት በሀይል ይበረታል። ይህ ጊዜ ያ ቀን አስቸጋሪ ቀን ነው። በተለይ በከሓዲያን ላይ ገር ያልሆነ ቀን ነው።

ذَرۡنِي وَمَنۡ خَلَقۡتُ وَحِيدٗا ﴿١١﴾ وَجَعَلۡتُ لَهُۥ مَالٗا مَّمۡدُودٗا ﴿١٢﴾ وَبَنِينَ شُهُودٗا ﴿١٣﴾
وَمَهَّدتُّ لَهُۥ تَمۡهِيدٗا ﴿١٤﴾ ثُمَّ يَطۡمَعُ أَنۡ أَزِيدَ ﴿١٥﴾ كَلَّآۖ إِنَّهُۥ كَانَ لِأٓيَٰتِنَا عَنِيدٗا ﴿١٦﴾
سَأُرۡهِقُهُۥ صَعُودًا ﴿١٧﴾ إِنَّهُۥ فَكَّرَ وَقَدَّرَ ﴿١٨﴾ فَقُتِلَ كَيۡفَ قَدَّرَ ﴿١٩﴾ ثُمَّ قُتِلَ كَيۡفَ قَدَّرَ ﴿٢٠﴾
ثُمَّ نَظَرَ ﴿٢١﴾ ثُمَّ عَبَسَ وَبَسَرَ ﴿٢٢﴾ ثُمَّ أَدۡبَرَ وَٱسۡتَكۡبَرَ ﴿٢٣﴾ فَقَالَ إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا سِحۡرٞ يُؤۡثَرُ ﴿٢٤﴾
إِنۡ هَٰذَآ إِلَّا قَوۡلُ ٱلۡبَشَرِ ﴿٢٥﴾ سَأُصۡلِيهِ سَقَرَ ﴿٢٦﴾ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا سَقَرُ ﴿٢٧﴾ لَا تُبۡقِي
وَلَا تَذَرُ ﴿٢٨﴾ لَوَّاحَةٞ لِّلۡبَشَرِ ﴿٢٩﴾

**11-29.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ብቸኛ ሆኖ (ብቻየን ሁኜ)*1 ከፈጠርኩት ሰው ጋር ተወኝ። (እኔ ከእሱ ተንኮል እበቃለሁ)። ለእርሱም የተዘረጋን ገንዘብ በዓይነቱ ያደረግኩለት። በአደባባዩ ተገኝ የሆኑ ወንዶች ልጆችንም (የሰጠሁት)። ለእርሱም ኑሮውን መዘርጋትን የዘረጋሁለት እና ከዚያ ልጨምርለት ይከጅላል። ይከልከል፤ እርሱ ለአንቀፆቻችን በእርግጥ ተቃዋሚ ነበርና። በእርግጥ ችግርን አስገድደዋለሁ (የገሀነም አቀበትን እንዲወጣ አስገድደዋለሁ)። እርሱ በቁርኣን ጉዳይ አሰበ፤ ገመተም። እናም ተረገመ። እንዴት ገመተ!። ከዚያ ተረገመ። እንዴት ገመተ! ከዚያ እንደገና በቁርኣን ጉዳይ ተመለከተ። ከዚያ ፊቱን አጨፈገገ አኮማተረም። ከዚያ በአላህ ከማመን ዞረ። ኮራም። ይህ ከሌላ ሰው የሚቀዳ ድግምት እንጂ ሌላ አይደለም።*2 ይህ የሰው ቃል እንጂ ሌላ አይደለም አለ። ሰቀር በተባለ የገሀነም ዋሻ ውስጥ በእርግጥ አስገባዋለሁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰቀር ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ? (ያገኘችውን ሁሉ) አታስቀርም። አትተውምም። የሰዎችን ቆዳ በጣም አክሳይ ናት።

*1 ገንዘብ ሀብት ልጅ ...የሌለው ማለት ሊሆን ይችላል ወይም ብቻየን ሁኜ ያስገኜሁት ወይም ብቸኛው ተብሎ ይታወቅ ስለ ነበረ ነው ይህን ስያሜ የሰጠው ተብሏል።

*2 ይህ አባባል ቁርኣንን የሰው ንግግር ነው የሚሉትን ሁሉ ያጠቃልላል። አቡዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ በሐጅ ወራት በየህጃጆች ዘንድ እየሄዱ (ማን ነው የአላህን ንግግር ለህዝቦች እንዳደርስ የሚረዳኝ። ቁረይሾች የጌታዬን ንግግር እንዳላደርስ አድርገውኛል» ይሉ ነበር።

ከልብስ ደራቢው ምዕራፍ (11) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ወሊድ ኢብኑ ሙጊራ ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥቶ ሳለ ነብዩ የቁርኣን አናቅፅን አንብበውለት ትንሽ ለስለስ ያለ መሰለ። ይኸው ክስተት ለአቡ ጀህል ስለደረሰው በፍጥነት ወደ እሱ በመምጣት አጎቴ ሆይ ሰዎች ለአንተ ገንዘብ ሊሰጡህ እያሰባሰቡ ነው። ምክንያቱም ወደ ሙሐመድ አዘንብለሃል መባል ስለተሰማ ነው አለው። በዚህ ጊዜ ይህ ሰው አስር ወንድ ልጆች ያዉም ሁል ጊዜ ከአጠገቡ የማይለዩት ነበሩትና ነው። (ሱዩጢ)

عَلَيۡهَا تِسۡعَةَ عَشَرَ ٣٠ وَمَا جَعَلۡنَآ أَصۡحَٰبَ ٱلنَّارِ إِلَّا مَلَٰٓئِكَةٗۙ وَمَا جَعَلۡنَا عِدَّتَهُمۡ
إِلَّا فِتۡنَةٗ لِّلَّذِينَ كَفَرُواْ لِيَسۡتَيۡقِنَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ وَيَزۡدَادَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوٓاْ إِيمَٰنٗا
وَلَا يَرۡتَابَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ وَٱلۡمُؤۡمِنُونَ وَلِيَقُولَ ٱلَّذِينَ فِي قُلُوبِهِم مَّرَضٞ وَٱلۡكَٰفِرُونَ
مَاذَآ أَرَادَ ٱللَّهُ بِهَٰذَا مَثَلٗاۚ كَذَٰلِكَ يُضِلُّ ٱللَّهُ مَن يَشَآءُ وَيَهۡدِي مَن يَشَآءُۚ وَمَا يَعۡلَمُ جُنُودَ
رَبِّكَ إِلَّا هُوَۚ وَمَا هِيَ إِلَّا ذِكۡرَىٰ لِلۡبَشَرِ ٣١

**30-31.** በእርሷም ላይ አስራ ዘጠኝ (ዘበኞች) አሉባት፡፡ የእሳትንም ዘበኞች መላዕክት እንጂ ሌላ አላደረግንም፡፡ ቁጥራቸውንም ለእነዚያ በአላህ ለካዱት ሰዎች መፈተኛ* እንጂ ለሌላ አላደረግንም፡፡ እነዚያ መጽሐፍን የተሰጡት ሰዎች እንዲያረጋግጡ፤ እነዚያም በትክክል ያመኑት እምነትን እንዲጨምሩ፤ እነዚያም መጽሐፍን የተሰጡትና ምዕመናኖቹ እንዳይጠራጠሩ፤ እነዚያም በልቦቻቸው ውስጥ በሽታ ያለባቸው መናፍቃንና ከሓዲያን አላህ በዚህ ቁጥር ምን ምሳሌ ሻቷል? እንዲሉ እንጂ (አላደረግንም)፡፡ ልክ እንደዚሁ አላህ የሚፈልገውን ያጠማል፡፡ የሚፈልገውንም ያቀናል፡፡ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የጌታህንም ሰራዊት ልክ ከእርሱ በቀር ማንም አያውቅም፡፡ የሰቀር እሳት ለሰዎች መገሰጫ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡

* አንድ ከሃዲ አስራ ሰባቱን እኔ አለኋችሁ ሁለቱን ብቻ እርዳኝ በማለት አፊዞ ስለነበር ነው ይህ አባባል የወረደው፡፡ (ኢብኑ ቁተይባህ፡፡)

ከልብስ ደራቢው (30) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አንድ ቀን የተወሰኑ አይሁድ ወደ ነብዩ (ﷺ) በመምጣት የገሀነም ዘበኞች ስንት ናቸው ብለው በመጠየቅ ሲያፋጥጧቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ተብሏል፡፡ (ሱዩጢ)

كَلَّا وَٱلۡقَمَرِ ٣٢ وَٱلَّيۡلِ إِذۡ أَدۡبَرَ ٣٣ وَٱلصُّبۡحِ إِذَآ أَسۡفَرَ ٣٤ إِنَّهَا لَإِحۡدَى ٱلۡكُبَرِ ٣٥
نَذِيرٗا لِّلۡبَشَرِ ٣٦ لِمَن شَآءَ مِنكُمۡ أَن يَتَقَدَّمَ أَوۡ يَتَأَخَّرَ ٣٧

**32-37.** (ከክህደት) ይከልከሉ፡፡ በጨረቃ፤ በሌሊቱም በሄደ ጊዜ፤ በንጋቱም ባበራ ጊዜ፡፡ (እምላለሁ) እርሷ (ሰቀር) ከታላላቆች አደጋዎች አንዱ አስፈራሪ ነው ከናንተ መካከል ወደ በጎ ነገር መቅደምን ወይም ወደ ኋላ መቅረትን ለፈለገ ሰው ሁሉ፡፡

كُلُّ نَفْسِۭ بِمَا كَسَبَتْ رَهِينَةٌ ﴿٣٨﴾ إِلَّآ أَصْحَٰبَ ٱلْيَمِينِ ﴿٣٩﴾ فِى جَنَّٰتٍ يَتَسَآءَلُونَ ﴿٤٠﴾
عَنِ ٱلْمُجْرِمِينَ ﴿٤١﴾ مَا سَلَكَكُمْ فِى سَقَرَ ﴿٤٢﴾ قَالُوا۟ لَمْ نَكُ مِنَ ٱلْمُصَلِّينَ ﴿٤٣﴾
وَلَمْ نَكُ نُطْعِمُ ٱلْمِسْكِينَ ﴿٤٤﴾ وَكُنَّا نَخُوضُ مَعَ ٱلْخَآئِضِينَ ﴿٤٥﴾ وَكُنَّا نُكَذِّبُ
بِيَوْمِ ٱلدِّينِ ﴿٤٦﴾ حَتَّىٰٓ أَتَىٰنَا ٱلْيَقِينُ ﴿٤٧﴾

**38-47.** ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ ተያዥ ናት። እነዚያ መዝገባቸውን በቀኝ እጃቸው የሚሰጡት ብቻ ሲቀሩ። እነርሱማ በገነቶች ውስጥ ሁነው እርስ በራሳቸው ከአመፀኞች ሁኔታ ይጠያየቃሉ። ከዚያ ለእነርሱ እንዲህ ይሏቸዋል። በሰቀር ውስጥ ምን አስገባችሁ? ከሰጋጆች አልነበርንም። ለድሆችም የምናበላ አልነበርንም። ከዘባራቂዎችም ጋር እንዘባርቅ ነበር። በፍርዱ ቀንም እናስተባብል ነበርና ነው ይላሉ እርግጠኛው ነገር ሞት እስከመጣብን ድረስ።

فَمَا تَنفَعُهُمْ شَفَٰعَةُ ٱلشَّٰفِعِينَ ﴿٤٨﴾ فَمَا لَهُمْ عَنِ ٱلتَّذْكِرَةِ مُعْرِضِينَ ﴿٤٩﴾ كَأَنَّهُمْ حُمُرٌ
مُّسْتَنفِرَةٌ ﴿٥٠﴾ فَرَّتْ مِن قَسْوَرَةٍۭ ﴿٥١﴾ بَلْ يُرِيدُ كُلُّ ٱمْرِئٍ مِّنْهُمْ أَن يُؤْتَىٰ صُحُفًا مُّنَشَّرَةً ﴿٥٢﴾
كَلَّا ۖ بَل لَّا يَخَافُونَ ٱلْءَاخِرَةَ ﴿٥٣﴾ كَلَّآ إِنَّهُۥ تَذْكِرَةٌ ﴿٥٤﴾

**48-54.** እናም በዚያ ቀን የአማላጆች ሁሉ ምልጃ አትጠቅማቸውም። ከቁርኣን ከግሳጼም የሚያፈገፍጉበት ምን ምክኒያት አላቸው? እነርሱ ልክ ከአንበሳ የሸሹ ደንባሪዎች የሜዳ አህዮች ይመስላሉ። ይልቁንም ከእነርሱ መካከል ለእያንዳንዱ ሰው የተዘረጉ ፁሑፎችን በእጁ እንዲሰጥ ይፈልጋል*። ከዚህ መሰል ተግባራቸው ይከልከሉ። ይልቁንም የመጨረሻይቱን ዓለም ቅጣት አይፈሩም።

* ብዙ የተፍሲር ምሁራን እንደሚሉት የመካ ሰወች ለነቢዩ (ﷺ) ነብይነት የሚያስረዳ ለእየግላችን ደብዳቤ ሊደርሰን ይገባል ብለው ስለ ነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው ይላሉ።

فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ﴿٥٥﴾ وَمَا يَذْكُرُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ ۚ هُوَ أَهْلُ ٱلتَّقْوَىٰ وَأَهْلُ ٱلْمَغْفِرَةِ ﴿٥٦﴾

**55-56.** ስለዚህ የፈለገ ሰው ቁርኣንን ይገሰፅበታል። ሆኖም ሰዎች አላህ ካልፈለገ በስተቀር አይገሰፁም። እርሱ (አላህ) የመፈራት ባለቤት ነው። (ለፈሩትም) የምህረት ባለቤት ነው።*

* አህመድ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) በዚህ አንቀፅ ላይ «አላህ እኔ በብቸኝነት ልፍራ የሚገባኝ እንጂ በኔ ስልጣን ማንም ሊጋራኝ አይገባኝም። ይህን ላደረገ ሁሉ ደግሞ ልምረው የሚገባኝ አምላክ ነኝ እያለን ነው ብለዋል»ብለዋል።

**ከልብስ ደራቢው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-56) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ**

1. ኢስላማዊ አስተምህሮትን የሚያስተምሩ ሰዎች ሁሉ የቀልብ ንፅህና ከማስፈለጉም በላይ የአካልም ሆነ የልብስ ንፅህና እንደሚያስፍለግ፤
2. ነብዩ (ﷺ) ከስነ ምግባሮች ሁሉ በከፍተኛ በመልካም ስነ ምግባር ላይ መሆናቸውን፤
3. ብዙ ከሓዲያን እውነቶችን ላለመቀበል የሚከለክሏቸው በሽታዎች ኩራት፤ ለስልጣን መጓጓት ምቀኝነት መሆኑን፤
4. ታታሪነት ከሙስሊም ባህሪያት አንዱ መሆኑን፤
5. በአላህ ስሞችና ባህሪያት ዙሪያ ሊኖሩ የሚገባ ክብርና ግርማ ሞገስ፤
6. ሙዕሚን አካላቱም ይሁን ልብሱና ቦታው ንፁህ መሆን እንዳለበት፤
7. ለሙስሊም ኩራት የማይገባ ስለ መሆኑ፤
8. ለሙስሊም በምንም ነገር ላይ ትዕግስትን መላበስ እንደሚያስፈልገው፤
9. ንብረትና ልጅ አላህ የጠበቀው ሲቀር የኩራት መነሻዎች ስለመሆናቸው፤
10. የአላህን ተአምራት የሚክድ ሁሉ የከሃዲ ከሃዲ ስለመሆኑ፤
11. የቁረይሾች ከሃዲ ወሊድ ኢብኑ ሙጊራህ ምን እንደደረሰበት ማስተማር፤
12. ገንዘብ ከአላህ ፀጋዎች መካከል አንደኛው መሆኑና ማመስገኑ ተገቢ ስለ መሆኑ፤
13. ልጆች የዚህች አለም ውበትና ጌጥ መሆናቸውን፤
14. እንደ ቁርኣን ሁሉ ተውራትም ሆነ ኢንጂል እምነት የሚጨምርና የሚቀንስ መሆኑን ማስተማራቸውን፤
15. የገሀነም ዘበኞች ቁጥር ከአላህ ሌላ ማንም እንደማያውቃቸው፤
16. ገሀነም ለሰዎች ማስራሪያ ስለ መሆኑ፤
17. የገሀነም ዘበኞች ኃይለኛ መላኢኮች መሆናቸውን፤
18. ለገሀነም ከሚያበቁ ነገሮች መካከል ከሓዲያን እንደ አህያ እንደሚመሰሉ፤
19. የትኛዋም ነፍስ በስራዋ እንደምትጠየቅ፤
20. ከታላለቅ ወንጀሎች መካከል ሶላትን ማሳለፍ፤ ዘካን መከልከል ና ሙቶ መነሳትን መካድ መሆኑን፤
21. በሺርክ ለሚሞቱ ሁሉ አሸማጋይ ሽማግሌ እንደሌላቸው፤
22. የሰው ልጅ እምነት የመበላሸት መነሻው የእምነት ድክመት ስለ መሆኑ፤
23. ኩራት የሚገባውና ወንጀልን መማር የሚችለው አንድ አላህ ብቻ ስለ መሆኑ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የልብስ ደራቢው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (75)
# የትንሳኤ ቀን ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ቂያመህ)

سُورَةُ الْقِيَامَةِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (40) ናቸው።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

لَآ أُقْسِمُ بِيَوْمِ ٱلْقِيَٰمَةِ ﴿١﴾ وَلَآ أُقْسِمُ بِٱلنَّفْسِ ٱللَّوَّامَةِ ﴿٢﴾ أَيَحْسَبُ ٱلْإِنسَٰنُ أَلَّن نَّجْمَعَ
عِظَامَهُۥ ﴿٣﴾ بَلَىٰ قَٰدِرِينَ عَلَىٰٓ أَن نُّسَوِّىَ بَنَانَهُۥ ﴿٤﴾

**1-4.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሁኔታው ከሓዲያን እንደሚሉት) አይደለም። በትንሳኤ ቀን እምላለሁ። (ሁኔታው ከሓዲያን እንደሚሉት አይደለም)። ራሷን ወቃሽ በሆነች ነፍስም እምላለሁ። (በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ)። ሰው አጥንቶችን አለመሰብሰባችንን አሰበን? እንዴታ ጣቶቹን ፊት እንደነበሩ በማስተካከል ላይ ቻዮች ስንሆን (እንሰበስባቸዋለን)።

ከትንሳኤ ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አምር ቢን ረቢይአህ የተባለ ሰው ወደ ነብዩ መጥቶ ቂያማ መቼ ነው? ሁኔታውስ እንዴት ነው? በማለት ጠየቃቸውና ዘርዘር አድርገው ሲነግሩት ያ ቀን ባየሁ ኖሮ አላምንህም ነበር። ይህን አጥንት እስከሚሰበስብ ድረስ ሲላቸው ነው። (ዋሒዲ)

بَلْ يُرِيدُ ٱلْإِنسَٰنُ لِيَفْجُرَ أَمَامَهُۥ ﴿٥﴾ يَسْـَٔلُ أَيَّانَ يَوْمُ ٱلْقِيَٰمَةِ ﴿٦﴾ فَإِذَا بَرِقَ ٱلْبَصَرُ ﴿٧﴾
وَخَسَفَ ٱلْقَمَرُ ﴿٨﴾ وَجُمِعَ ٱلشَّمْسُ وَٱلْقَمَرُ ﴿٩﴾ يَقُولُ ٱلْإِنسَٰنُ يَوْمَئِذٍ أَيْنَ ٱلْمَفَرُّ ﴿١٠﴾
كَلَّا لَا وَزَرَ ﴿١١﴾ إِلَىٰ رَبِّكَ يَوْمَئِذٍ ٱلْمُسْتَقَرُّ ﴿١٢﴾

**5-12.** ይልቁን ሰው በፊቱ ባለ ነገር በትንሳኤ ቀን ሊያስተባብል ይፈልጋል። የትንሳኤው ቀን መቼ ነው? ሲል ይጠይቃል። ዓይንም በዋለለ ጊዜ። ጨረቃም በጨለመ ጊዜ። ፀሐይና ጨረቃም በተሰበሰቡ ጊዜ፤ የሰዎች በዚያ ቀን መሸሻው የት ነው? ይላል። ይከልከል፤ ምንም መጠጊያ የለም። በዚያ ቀን መርጊያው ወደ ጌታህ ብቻ ነው ይባላል።

يُنَبَّؤُا۟ ٱلْإِنسَٰنُ يَوْمَئِذٍۭ بِمَا قَدَّمَ وَأَخَّرَ ﴿١٣﴾ بَلِ ٱلْإِنسَٰنُ عَلَىٰ نَفْسِهِۦ بَصِيرَةٌ ﴿١٤﴾
وَلَوْ أَلْقَىٰ مَعَاذِيرَهُۥ ﴿١٥﴾

**13-15.** የሰው ልጅ በዚያ ቀን ያስቀደመውንና ያስቆየውን ሁሉ ይነገረዋል። በእርግጥ ሰው በነፍሱ ላይ አስረጅ ነው። ምክንያቶቹን ሁሉ ቢያመጣ እንኳን (አይስሰማም)።*

✷ የሰው ልጅ የቱንም ያክል ከስህተቱ ላለመታረም ቢሟገት እንኳን ለጥፋቶቹ አያሌ ምክኒያቶቹን ቢደረድርም የስህቱን እውነታ በትክክል ከእሱ ያወቀ የለም። ይህ እውነታ ሰዎች በብዙ አጋጣሚ ሊከሰቱባቸው ይችላሉ።

1. ለምሳሌ እውነትን በማስረጃ ሲቀርብ መቀበልን በተመለከተ፡አንዳንድ ሰዎች በምንም መልኩ ጥርጣሬ የሌለው ማስረጃ ከረሳው በኋላ ከራሱ ላይ ለመከላከልና ስሜቱ ብቻ ስለደገፈው የሚንፈራገጥ አለ።
2. ራስን ከማሸነፍ ጋር በተያያዘ መልኩ፡ ብዛት ያላቸው ሰዎች የራሳቸውን ነውር ትተው የሌሎችን ነዉር በመከታተል የተመረዙ አሉ። ቀታዳ የተባሉ ዐሊም ይህንን አንቀፅ ሲያብራሩ «ብትፈልግ የራሱን ነውር ዘንግቶ የሌሎችን ስህተት የሚያሳድድ ሁኖ ታገኜዋለህ» ብለዋል። ይህ ደግሞ የከሳራው ሁሉ ከሳራ ማለት ነው። በክር ኢብኑ ዐብደላህ «አንድን ሰው የሌሎችን ነዉር በመከታተል ተጠምዶ ካየኸው ተሸዉዷል» ብለዋል።

   ሰለፎች እንዲህ ይሉ ነበር «ከእውነቱ ሁሉ ጠቃሚው እውነት የራስክን ነዉር ለአላህ ማመን ነው» ብለዋል።

   የሰው ልጅ የግል ነዉሩን መፈተሽ አለበት። በየጊዜው ካለበት ነዉር እንዴት እንደሚጠራ መጣር አለበት።
3. ይህን አንቀፅ በትክክል መረዳት ስህተትን አምኖ መቀበልን ያስከትላል። ይህ ደግሞ የነቢያት ተግባር ነው። አባታችን አደምና እናታችን ሐዋእ «ጌታችን ሆይ፣ ነፍሶቻችንን በደልን። ባትምረንና ባታዝንልን በእርግጥ ከከሳሪዎቹ እንሆናለን አሉ።» አል-አዕራፍ 23. ብለዋል። ነቢዩ ኑህ «ጌታዬ ሆይ፣ በእርሱ ለእኔ እውቀት የሌለኝን ነገር የምጠይቅህ ከመሆን እኔ በአንተ እጠበቃለሁ። ለእኔም ባትምረኝና ባታዝንልኝ ከከሳሪዎቹ እሆናለሁ አለ።» ሁድ 47፤ ብለዋል። ነብዩ ሙሳ «ጌታዬ ሆይ! እኔ ነፍሴን በደልኩ ለኔም ማር አለ ለርሱም ምህረት አደረገለት፤ እርሱ መሓሪና አዛኝ ነውና።» አል-ቀሶስ 16. ብለዋል።

لَا تُحَرِّكْ بِهِۦ لِسَانَكَ لِتَعْجَلَ بِهِۦٓ ﴿١٦﴾ إِنَّ عَلَيْنَا جَمْعَهُۥ وَقُرْءَانَهُۥ ﴿١٧﴾
فَإِذَا قَرَأْنَٰهُ فَٱتَّبِعْ قُرْءَانَهُۥ ﴿١٨﴾ ثُمَّ إِنَّ عَلَيْنَا بَيَانَهُۥ ﴿١٩﴾

**16-19.** (በቁርአን ንባብ) ልትቸኩል ብለህ ምላስህን በእርሱ አታላውስ። በልብህ ውስጥ መሰብሰቡና ማስነበቡ በኛ ላይ ነውና። (መልዐኩ) ባነበበው ጊዜ ካለቀ በኋላ ንባቡን ተከተል። ከዚያ ለአንተ ማብራራት በእኛ ላይ ነው።

ከትንሳኤ ምዕራፍ (16) ኛው ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) መልዐኩ ጅብሪል ወህይ ይዞ በሚመጣበት ጊዜ እንዳይረሱት ቶሎ ቶሎ እየተከታተሉ በማንበብ ይጣደፉ ስለነበር ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

كَلَّا بَلْ تُحِبُّونَ ٱلْعَاجِلَةَ ﴿٢٠﴾ وَتَذَرُونَ ٱلْـَٔاخِرَةَ ﴿٢١﴾ وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ نَّاضِرَةٌ ﴿٢٢﴾
إِلَىٰ رَبِّهَا نَاظِرَةٌ ﴿٢٣﴾ وَوُجُوهٌ يَوْمَئِذٍۭ بَاسِرَةٌ ﴿٢٤﴾ تَظُنُّ أَن يُفْعَلَ بِهَا فَاقِرَةٌ ﴿٢٥﴾

**20-25.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከመጣደፍ ተከልከል፤ ይልቁንም (ሰዎች ስትባሉ) ፈጣኒቱን ዓለም ትወዳላችሁ። የመጨረሻይቱን ዓለም ግን ትተዋላችሁ። የተወሰኑ ፊቶች በዚያ ቀን አብሪዎች ናቸው። ወደ ጌታቸው ተመልካቾችም* ናቸው። ሌሎች ፊቶችም በዚያ ቀን አጨፍጋጊዎች ናቸው። በእነርሱም ላይ አደጋ እንደሚሰራባቸው ያረጋግጣሉ።

* ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐብደላህ አልበጀሊ እንዳስተላፉት ከአላህ መልዕክተኛ ጋር እያለን የአስራ አራት ቀን ጨረቃ ተመለከቱና እንዲህ አሉ፡- «አምላካችሁን በዕለተ ትንሳኤ ልክ ይህችን ጨረቃ እንደምታዩት በግልፅ ታዩታላችሁ። እርሱን ለማየትም አትጋፉም። ፀሐይ ከመውጣቷና ከመግባቷ በፊት ያሉ ሶላቶችን በመስገድ አለመሸነፍ የምትችሉ ከሆናችሁ እንደደረሱ አድርጉ»

كَلَّآ إِذَا بَلَغَتِ ٱلتَّرَاقِىَ ﴿٢٦﴾ وَقِيلَ مَنْ ۜ رَاقٍ ﴿٢٧﴾ وَظَنَّ أَنَّهُ ٱلْفِرَاقُ ﴿٢٨﴾
وَٱلْتَفَّتِ ٱلسَّاقُ بِٱلسَّاقِ ﴿٢٩﴾ إِلَىٰ رَبِّكَ يَوْمَئِذٍ ٱلْمَسَاقُ ﴿٣٠﴾

**26-30.** ሙስሊሞች አስተውሉ። (ነፍስ) ወደ ጉሮሮ በደረሰችና፤ አሻሪው ማነው? በተባለ ጊዜ፤ ህመምተኛው የሰፈረበት ነገር ከዚህ ዓለም መለየት መሆኑን ባረጋገጠ ባትም ከባት በተጣበቀች ጊዜ፤ በዚያ ቀን መነዳት ወደ ጌታህ ፍርድ ብቻ ነው።

فَلَا صَدَّقَ وَلَا صَلَّىٰ ﴿٣١﴾ وَلَٰكِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰ ﴿٣٢﴾ ثُمَّ ذَهَبَ إِلَىٰٓ أَهْلِهِۦ يَتَمَطَّىٰٓ ﴿٣٣﴾
أَوْلَىٰ لَكَ فَأَوْلَىٰ ﴿٣٤﴾ ثُمَّ أَوْلَىٰ لَكَ فَأَوْلَىٰٓ ﴿٣٥﴾

**31-35.** እናም አላመነምም፤ አልሰገደምም። ግን በአላህ አስተባበለ፤ ከእምነት ዞረም። ከዚያ እየተንጎማለለ ወደ ቤተሰቡ ሄደ። የምትጠላውን ነገር አላህ ያስከትልህ፤ ለአንተ ተገቢህም ነው። ከዚያ ጥፋት ይጠጋህ ለአንተ የተገባህም ነው።

أَيَحْسَبُ ٱلْإِنسَٰنُ أَن يُتْرَكَ سُدًى ﴿٣٦﴾ أَلَمْ يَكُ نُطْفَةً مِّن مَّنِىٍّ يُمْنَىٰ ﴿٣٧﴾
ثُمَّ كَانَ عَلَقَةً فَخَلَقَ فَسَوَّىٰ ﴿٣٨﴾ فَجَعَلَ مِنْهُ ٱلزَّوْجَيْنِ ٱلذَّكَرَ وَٱلْأُنثَىٰٓ ﴿٣٩﴾
أَلَيْسَ ذَٰلِكَ بِقَٰدِرٍ عَلَىٰٓ أَن يُحْـِۧىَ ٱلْمَوْتَىٰ ﴿٤٠﴾

**36-40.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰው እንደፈለገ እንዲኖር ልቅ ሆኖ የሚተው ይመስለዋልን? የሚፈስስ ከሆነ የፍትወት ጠብታ አልነበረምን? ከዚያ የረጋ ደም ሆነ። ከዚያ አላህ ሰው አድርጎ ፈጠረው፤ አስተካከለውም። ከእርሱም ሁለት ዓይነቶች ወንድና ሴት አደረገ። ይህ ሀያል (ጌታ) ሙታንን ሕያው በማድረግ ላይ ቻይ አይደለምን?*

* ‹ከትንሳኤ ከ (34-35) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- «በእርሷም ላይ አስራ ዘጠኝ ዘበኞች አሉባት...»፡- የሚለው ቁርአን ሲወርድ አቡጀህል መኮችን ሰብስቦ ያጥፋችሁ የአቡከብሻ ልጅ የጀሀነም ዘበኞች አስራ ዘጠኝ ናቸው ይላል። እናንተ ብዙ ህዝቦች ናችሁ። አስር አስሮች እንኳን አንድ አንዱን ማሸነፍ ያቅታችኋልን በማለት ስላፌዘ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

**ከትንሳኤ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-40) አናቅፅ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙቶ መነሳትን ማረጋገጥ፤
2. አላህ ለሰው ልጅ የዋለው ውለታ መዘርዘር፤
3. የሰዎች የጣት አሻራ መለያየት ከአላህ ተዐምራት መካከል አንዱና አስገራሚ መሆኑን፤
4. የሰው ልጅ በጀመሪው ኸይር ስራ ምንዳ እንደሚያገኝ ሁሉ በመጥፎውም እንደሚጠየቅ፤
5. ስለ ቂያማ ቀን ትልቅነትና ክብደት፤
6. ነፍሶች ብዙ አይነት እንደሆኑ፤
7. አለማወቅ ምን ያህል ችግር እንዳለው፤
8. ዛሬ በአሻራና በምስክርነት እየተጠቀምንባት ያለውን ሁኔታ አስቀድሞ ማንሳቱ የሚያያሳየውን ተዓምር፤
9. የሞትን ሀቅነት አምላጭ እንደሌለውና አስተማሪነቱ፤
10. ከአስመሳዮች አያሌ ምልክቶች መካከል በአላህና በመላዕክተኛው አለማመን በሶላትና በመሰል የዲን ምልክቶች ችላ ማለት፤ በቁርአን ህግጋት መቀለድና ማፍዝ እንደሆነ፤
11. ኩራት የተጠላ አስከፊ ባህሪ መሆኑን፤
12. የሰው ልጅ የተፈጠረበት አላማ ያለው መሆኑን፤
13. የሰው ልጅን አመጣጥና አፈጣጠር በዝርዝር፤
14. በሰው ልጆች መካከል ፆታን መፍጠር ወንድና ሴት አድርጎ በመሀከላቸው ፍቅር እንደፈጠረና ዘር እንደሰጣቸው፤
15. ለመጀመሪያ ጊዜ የፈጠረ ጌታ መልሶ መቀስቀስ እንደሚችል እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የትንሳኤ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (76)
# የሰው ምዕራፍ
# (ሱረቱ አልኢንሳን)

سُورَةُ الإِنسَانِ

## የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (31) ናቸው።
## የሱረቱ አል ኢንሳን መግቢያ

ስሞቹንም በተመለከተ እንዲሁ ክርክር አለበት። የሰዎች ምዕራፍ፤ ሀል አታ ዐለል ኢነሳኒ፤ ሱረቱ ደህር፤ ሱረቱ አምሻጅ፤ ሱረቱ አብራር ይባላል።

ኢብኑ ዐሳኪር፤ ጦበራኒና ኢብኑ መርደወይህ ከኢብኑ ዑመር ዋቢ አድርገው በዘገቡት ሐዲስ «አንድ የሐበሻ ሰው ወደ ነብዩ መጥቶ ነብዩ ጠይቅ ተረዳ አሉት በዚህ ጊዜ እኛን በመልክ በስዕል በነቢይነት በለጣችሁን ግን አንተ ባመንክበት ባምን አንተ የምትሰራዉን ብሰራ ከአንተ ጋር ጀነት እሆናለሁን አላቸው። ነብዩም አዎ ነፍሴ በእጁ በሆነው በአላህ ይሁንብኝ የጥቁሩ ነጭ ከአንድሺ አመት ከሚያስከድ ርቀት ላይ ሁኖ ይታያል.... አሉት። በዚህ ጊዜ የዚህ ምዕራፍ ከመጀመሪያ -እስከ (20) ኛው አንቀፅ ድረስ ወረደ። ...በዚህ ጊዜ ሐበሺው ይቺ አይኔ አንተ የምታየዉን ታያለች አላቸው። እሳቸዉም አዎ አሉት በዚህ ጊዜ ታመመና በዚያው በሺታ ሞተ። ነብዩ ይህን ሰዉየ በጃቸው ሲቀብሩት አየቻለሁኝ። (ፈትሁልቀዲር።)

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

هَلۡ أَتَىٰ عَلَى ٱلۡإِنسَٰنِ حِينٞ مِّنَ ٱلدَّهۡرِ لَمۡ يَكُن شَيۡـٔٗا مَّذۡكُورًا ١ إِنَّا خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ مِن
نُّطۡفَةٍ أَمۡشَاجٖ نَّبۡتَلِيهِ فَجَعَلۡنَٰهُ سَمِيعَۢا بَصِيرًا ٢ إِنَّا هَدَيۡنَٰهُ ٱلسَّبِيلَ إِمَّا شَاكِرٗا وَإِمَّا
كَفُورًا ٣ إِنَّآ أَعۡتَدۡنَا لِلۡكَٰفِرِينَ سَلَٰسِلَاْ وَأَغۡلَٰلٗا وَسَعِيرًا ٤

**1-4.** በሰው ልጆች (አባት በአደም) ላይ የሚታወስ ነገር ሳይሆን ከዘመናት የተወሰነ ጊዜ (አላለፈዉም ነበርን) በእርግጥ አልፎታል*1። እኛ ሰውን*2 (በሕግጋት ግዳጅ) የምንሞክረው ስንሆን ከወንድና ከሴት ፈሳሽ ቅልቅሎች ከሆነች የፍትወት ጠብታ ፈጠርነው። ከዚያ ሰሚና ተመልካች አደረግነው። እኛ አመስጋኝ ወይም ከሓዲ ሲሆን መንገዱን መራነው። እኛ ለከሓዲያን ስንሰለቶችንና እንዘዝላዎችን፤ እሳትንም (አዘጋጅተናል)።

*1 እዚህ ቦታ ሰው የተባለው አባታችንን አደምን ነው የሚሉት ብዙ ናቸው።

ዑመር ኢብኑ ልኸጧብ ይህን አንቀፅ ሰምተው አንዲት ትቢያ አንስተው ድምፃቸዉን ከፍ አድርገው ምንው እንደዚች ትቢያ በሆንኩኝ፤ ምነው በዚያው በቀረን። ምነው እናቴ ባልወለደችን፤ ምንው ተረስቼ በቀረሁ አሉ። ኢብኑ ዘመነይን።

*2 እዚህ ላይ ያለው ሰው ደግሞ እኛን የአደምና የሐዋ ልጆችን ነው።

إِنَّ ٱلْأَبْرَارَ يَشْرَبُونَ مِن كَأْسٍ كَانَ مِزَاجُهَا كَافُورًا ﴿٥﴾
عَيْنًا يَشْرَبُ بِهَا عِبَادُ ٱللَّهِ يُفَجِّرُونَهَا تَفْجِيرًا ﴿٦﴾
يُوفُونَ بِٱلنَّذْرِ وَيَخَافُونَ يَوْمًا كَانَ شَرُّهُۥ مُسْتَطِيرًا ﴿٧﴾
وَيُطْعِمُونَ ٱلطَّعَامَ عَلَىٰ حُبِّهِۦ مِسْكِينًا وَيَتِيمًا وَأَسِيرًا ﴿٨﴾
إِنَّمَا نُطْعِمُكُمْ لِوَجْهِ ٱللَّهِ لَا نُرِيدُ مِنكُمْ جَزَآءً وَلَا شُكُورًا ﴿٩﴾
إِنَّا نَخَافُ مِن رَّبِّنَا يَوْمًا عَبُوسًا قَمْطَرِيرًا ﴿١٠﴾

**5-10.** እነዚያ (ትክክለኛ አማኞች) በጎ አድራጊዎች መበረዣዋ ካፉር ከሆነች ጠጅ ይጠጣሉ። ከእርሷ እነዚያ የአላህ ባሮች የሚጠጡላት ና ወደ ፈለጉበት ማንቧቧትን የሚያንቧቧት ከሆነች የጠጅ ምንጭ (ይጠጣሉ)። ዛሬ በዚህ ዓለም እያሉ በስለታቸው ይሞላሉ። መከራው ተሰራጪ የሆነንም ቀን ይፈራሉ። ምግብንም በጣም ከመውደዳቸው ጋር (ይቅርብን ብለው) ለድሃ፤ ለየቲምና ለምርኮኛ ያበላሉ። የምናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ነው። ከናንተ ክፍያንም ሆነ ማመስገንን አንፈልግም። እኛ (ፊትን) የሚያጨፈግግን ብርቱ ቀን ከጌታችን እንፈራለንና (ይላሉ)።

فَوَقَىٰهُمُ ٱللَّهُ شَرَّ ذَٰلِكَ ٱلْيَوْمِ وَلَقَّىٰهُمْ نَضْرَةً وَسُرُورًا ﴿١١﴾ وَجَزَىٰهُم بِمَا صَبَرُوا۟ جَنَّةً
وَحَرِيرًا ﴿١٢﴾ مُّتَّكِـِٔينَ فِيهَا عَلَى ٱلْأَرَآئِكِ ۖ لَا يَرَوْنَ فِيهَا شَمْسًا وَلَا زَمْهَرِيرًا ﴿١٣﴾
وَدَانِيَةً عَلَيْهِمْ ظِلَـٰلُهَا وَذُلِّلَتْ قُطُوفُهَا تَذْلِيلًا ﴿١٤﴾ وَيُطَافُ عَلَيْهِم بِـَٔانِيَةٍ مِّن فِضَّةٍ
وَأَكْوَابٍ كَانَتْ قَوَارِيرَا۠ ﴿١٥﴾ قَوَارِيرَا۟ مِن فِضَّةٍ قَدَّرُوهَا تَقْدِيرًا ﴿١٦﴾ وَيُسْقَوْنَ فِيهَا
كَأْسًا كَانَ مِزَاجُهَا زَنجَبِيلًا ﴿١٧﴾ عَيْنًا فِيهَا تُسَمَّىٰ سَلْسَبِيلًا ﴿١٨﴾ ۞ وَيَطُوفُ عَلَيْهِمْ
وِلْدَٰنٌ مُّخَلَّدُونَ إِذَا رَأَيْتَهُمْ حَسِبْتَهُمْ لُؤْلُؤًا مَّنثُورًا ﴿١٩﴾ وَإِذَا رَأَيْتَ ثَمَّ رَأَيْتَ
نَعِيمًا وَمُلْكًا كَبِيرًا ﴿٢٠﴾ عَـٰلِيَهُمْ ثِيَابُ سُندُسٍ خُضْرٌ وَإِسْتَبْرَقٌ ۖ
وَحُلُّوٓا۟ أَسَاوِرَ مِن فِضَّةٍ وَسَقَىٰهُمْ رَبُّهُمْ شَرَابًا طَهُورًا ﴿٢١﴾
إِنَّ هَـٰذَا كَانَ لَكُمْ جَزَآءً وَكَانَ سَعْيُكُم مَّشْكُورًا ﴿٢٢﴾

**11-22.** አላህም የዚያን ቀን ክፋት ጠበቃቸው፤ ፊታቸው ማማርንና መደሰትንም ገጠማቸው። በመታገሳቸውም ምክንያት ገነትንና የሀር ልብስን መነዳቸው። በውስጧ በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ተደጋፊዎች፤ በውስጧ የፀሀይን ሐሩርንም ሆነ ብርድን አያዩም። ዛፎቿም ለእነርሱ የቀረበች፤ ፍራፍሬዎችዋም ለለቃሚዎች መገራትን የተገራች ስትሆን ገነትን (መነዳቸው)። በእነርሱም ላይ ከብር በተሰሩ ዕቃዎች (ሳሐኖች)፤ የብርጭቆዎች በሆኑ ኩባያዎችም ይዝዞርባቸዋል። መለካትን የለኳቸው በሆኑ የብር ብርጭቆዎች (ይዝዞርባቸዋል)። በእርሷም መበረዣዋ ዘንጀቢል የሆነች ወይን ጠጅ ይጥጣሉ። በውስጧ ያለችውን ሰልሰቢል ተብላ የምትጠራውን ምንጭ። በእነርሱም ላይ (ባሉበት ሁኔታ) የሚዘወትሩ ወጣት ልጆች ይዘዋወራሉ። ባየሃቸው ጊዜ የተበተነ ሉል ናቸው ብለህ ታስባቸዋለህ። እዚያንም በተመለከትክ ጊዜ ፀጋንና ታላቅ ንግስና ታያለህ። አረንጓዴዎች ሆኑ ቀጭን ሀር ልብሶችና ወፍራም ሀርም በላያቸው ላይ አለ። ከብር የሆኑ አንባሮችንም ይሸለማሉ። ጌታቸውም (ከራሱ አልፎ) ሌላን አጥሪ የሆነን መጠጥ ያጠጣቸዋል። ይህ ለእናንተ ዋጋ ሆነ። ስራችሁም ምስጉን ሆነ ይባላሉ።

ከሰው ልጅ ምዕራፍ (20) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ዑመር ነብዩን (ﷺ) በሰሌን ላይ ተኝተው ጎናቸው ጎርቦ (ሰምበር አውጥቶ) ሲያይዋቸው አለቀሱ። በዚህ ጊዜ ለምን ታለቅሳለህ ብለው ሲጠይቋቸው የኪስራን፤ የሁርሙዝንና የሐበሻን ንጉሶች ምቾትና የእርሶዎን የአላህ መልዕክተኛ ሆነው ሳለ በሰሌን ላይ መሆንዎን ሳይ ነው አሏቸው። በዚህ ጊዜ ነብዩ ለእነሱ ይህች ዓለም ሁናላቸው ለእኛ ደግሞ አኺራ ቢሆን ደስ አይልህምን? በማለት ስለመለሱላቸው ነው። (ዋሒዲ)

إِنَّا نَحۡنُ نَزَّلۡنَا عَلَيۡكَ ٱلۡقُرۡءَانَ تَنزِيلٗا ﴿٢٣﴾ فَٱصۡبِرۡ لِحُكۡمِ رَبِّكَ
وَلَا تُطِعۡ مِنۡهُمۡ ءَاثِمًا أَوۡ كَفُورٗا ﴿٢٤﴾

**23-24.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) እኛ ይህንን ቁርኣን ባንተ ላይ ማውረድን እኛው አወረድነው። ለጌታህ ፍርድ ታገስ። ከእነርሱም መካከል ኃጢአተኛን ወይም ከሓዲን አትታዘዝ።

ከሰው ልጅ ምዕራፍ (24) ኛው አንቀፅ ወረደበት ምክንያት፡- አቡጀህል ሙሐመድ ሲሰግድ ባየሁት ጊዜ በአንገቱ ላይ ነው የምቆመው በማለቱ ነው። (ሱዩጢ)

وَٱذۡكُرِ ٱسۡمَ رَبِّكَ بُكۡرَةٗ وَأَصِيلٗا ﴿٢٥﴾ وَمِنَ ٱلَّيۡلِ فَٱسۡجُدۡ لَهُۥ وَسَبِّحۡهُ لَيۡلٗا طَوِيلًا ﴿٢٦﴾

**25-26.** የጌታህን ስም በጠዋትና ከቀትር በኋላ አውሳ። ከሌሊቱም ለእርሱ ብቻ ስገድ፤ በረዢም ሌሊትም አወድስ።

إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ يُحِبُّونَ ٱلۡعَاجِلَةَ وَيَذَرُونَ وَرَآءَهُمۡ يَوۡمٗا ثَقِيلٗا ﴿٢٧﴾

**27.** እነዚያ ይህችን ፈጣኒቱን ዓለም ይወዳሉ፤ ከባድ አስቸጋሪ ቀንም በስተፊታቸው ሆኖ ችላ ይላሉ።

نَّحۡنُ خَلَقۡنَٰهُمۡ وَشَدَدۡنَآ أَسۡرَهُمۡۖ وَإِذَا شِئۡنَا بَدَّلۡنَآ أَمۡثَٰلَهُمۡ تَبۡدِيلًا ﴿٢٨﴾

**28.** እኛ ፈጠርናቸው። የአካሎቻቸቸዉን መለያያቸውንም አጠነከርን። በፈለግን ጊዜ መሰሎቻቸውን መለወጥን እንለውጣለን።

إِنَّ هَٰذِهِۦ تَذۡكِرَةٞۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ سَبِيلٗا ﴿٢٩﴾ وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُۚ
إِنَّ ٱللَّهَ كَانَ عَلِيمًا حَكِيمٗا ﴿٣٠﴾

**29-30.** ይህ መገሰጫ ነው። የፈለገ ሰው ወደ ጌታው መንገድ ይይዛል። አላህም ካልፈለገ በስተቀር አትሹም፤ አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነውና።

يُدۡخِلُ مَن يَشَآءُ فِي رَحۡمَتِهِۦۚ وَٱلظَّٰلِمِينَ أَعَدَّ لَهُمۡ عَذَابًا أَلِيمَۢا ﴿٣١﴾

**31.** (አላህ) የሚፈልገውን ሰው በእዝነቱ ውስጥ ያስገባዋል። በዳዩችንም (ዝቶባቸዋል)፤ ለእነርሱ አሳማሚ ቅጣትትን አዘጋጅቶላቸዋል።

**ከሰዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-31) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. የሰው ልጅ አባት የሆኑት አደምና ከዚያም በኋላ የሚወለዱት ሰዎች አፈጣጠር ከአፈርና ከደካማ ፈሳሽ እንደሆነ በዝርዝር መጠቆምና የሰው ልጅ ምንም አቅም የሌለው ደካማ በመሆኑ በጌታው ላይ ሊያምፅ እንደማይገባው፤
2. ከአዕምሮ ጋር የመስሚያና የማያ አካሎች ለሰው ልጅ በጣም አስፈላጊ ስለመሆናቸው፤
3. የሰው ልጅ ፊት ለፊቱ ሁለት መንገዶች እንዳሉና የፈለገውን መርጦ መከተል እንደሚችል የግል ምርጫው መሆኑን፤
4. ከአባታችን አደም በኋላ መላው ህዝብ ከአባትና ከእናት ፈሳሽ የተደባልቀ ስለሆነ የሰው ልጅ ዘር መሆኑን፤
5. ስለትን በወንጀል ካልሆነ በስተቀር መሙላት ግዴታ ስለመሆኑ፤
6. ችግረኞችን መመገብና የቲምን መርዳት አስፈላጊ ፅድቅ ተግባር ስለ መሆኑ፤
7. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥና እንድናምንበት ግፊት ማሳደር፤
8. በወርቅ ወይም በብር እቃነት ወይም በሌላ ነገሮች ላይ በዱንያ ለወንድ መጠቀም ክልክል ስለመሆኑ፤
9. ኸምርን መጠጣት በዱንያ የተከለከለ ስለመሆኑና በአኼራ ግን ይህን ስም የያዘ ጣፋጭ መጠጥ እንዳለ፤

10. ሰራተኞችን በመልካም መያዝ ተፈላጊ ስለመሆኑ፤
11. ለወንድ ልጅ ሐርን መልበስ ክልክል መሆኑንና ለሴት የተፈቀደ መሆኑን፤
12. ከሃዲንና ወንጀለኛን በምንም መልኩ መታዘዝ እንደሌለብን፤
13. ሙዕሚን የሆነ ሰው በሶላትና በዚክር እንዲሁም በዱዓ መታገዝ እንዳለባቸው፤
14. የሌሊት ሶላት አስፈላጊነት፤
15. የአላህ ፍላጎት ከፍላጎቶች ሁሉ በላይና ተቀዳሚ ስለመሆኑ፤
16. ቁርኣን ምእመናን ማስታወሺያና ማንቂያ ስለ መሆኑ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የሰው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (77)
## የተላኪዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሙርሰላት)

سُورَةُ المُرۡسَلَاتِ

የወረደው በመካ ነው። የየ አናቅፅ ብዛት (50) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلۡمُرۡسَلَٰتِ عُرۡفٗا ١ فَٱلۡعَٰصِفَٰتِ عَصۡفٗا ٢ وَٱلنَّٰشِرَٰتِ نَشۡرٗا ٣ فَٱلۡفَٰرِقَٰتِ فَرۡقٗا ٤
فَٱلۡمُلۡقِيَٰتِ ذِكۡرًا ٥ عُذۡرًا أَوۡ نُذۡرًا ٦ إِنَّمَا تُوعَدُونَ لَوَٰقِعٞ ٧

**1-7.** ተከታታይ ሆነው በተላኩት (ነፋሶች)፤ በኃይል መንፈስን ነፋሾች በሆኑት (ነፋሶች)፤ መበተንን በታኝ በሆኑት። መለየትን ለይዎች በሆኑት (መላዕክት)፤ ምክንያትን ለማስወገድ ወይም ለማስፈራራት መገሰጫን ወደ ነብያት አምጪዎች በሆኑት (መላዕክት) እምላለሁ ያ፣ የምትስፈራሩበት (ትንሳኤ) በእርግጥ ኗኝ ነው (ብየ እምላለሁ)።

فَإِذَا ٱلنُّجُومُ طُمِسَتۡ ٨ وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ فُرِجَتۡ ٩ وَإِذَا ٱلۡجِبَالُ نُسِفَتۡ ١٠
وَإِذَا ٱلرُّسُلُ أُقِّتَتۡ ١١ لِأَيِّ يَوۡمٍ أُجِّلَتۡ ١٢ لِيَوۡمِ ٱلۡفَصۡلِ ١٣ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ
ٱلۡفَصۡلِ ١٤ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ١٥

**8-15.** ከዋክብትም (ብርሃንዋን) በታበሰች ጊዜ፤ ሰማይም በተከፈተች ጊዜ፤ ጋራዎችም በተንኮታኮቱ ጊዜ። መልዕክተኞቹም ወቅት በተደረገላቸው ጊዜ፤ ለየትኛው ቀን ተቀጠሩ የሚባል ሲሆን፤ ለዚያ ለመለያው ቀን ተቀጠሩ በተባለ ጊዜ፤ በዚያ ቀን (በፍጡሮች መካከል በትክክል ይፈርዳል)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የመለያው ቀን ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ። ለአስተባባዮች ሁሉ በዚያን ቀን ወዮውላቸው።

أَلَمۡ نُهۡلِكِ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٦ ثُمَّ نُتۡبِعُهُمُ ٱلۡأٓخِرِينَ ١٧ كَذَٰلِكَ نَفۡعَلُ بِٱلۡمُجۡرِمِينَ ١٨
وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ١٩

**16-19.** የፊተኞቹን (ህዝቦች) አላጠፋንምን? ከዚያ ኋለኞቹን እናስከትላቸዋለን። በአመፀኞች ሁሉ ላይ ልክ እንደዚሁ ያለ እንሰራለን። ለአስተባባዩች ሁሉ በዚያን ቀን ወዮወላቸው።

أَلَمْ نَخْلُقكُّم مِّن مَّآءٍ مَّهِينٍ ﴿٢٠﴾ فَجَعَلْنَٰهُ فِى قَرَارٍ مَّكِينٍ ﴿٢١﴾ إِلَىٰ قَدَرٍ مَّعْلُومٍ ﴿٢٢﴾
فَقَدَرْنَا فَنِعْمَ ٱلْقَٰدِرُونَ ﴿٢٣﴾ وَيْلٌ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ ﴿٢٤﴾

**20-24.** (ሰዎች ሆይ!) ውሃ አልፈጠርናችሁምን? በተጠበቀ መርጊያ ውስጥም (በማህፀን) አደረግነው። እስከታወቀ ጊዜ ድረስ፤ መጠንነውም። ምን ያማርንም መጣኞች ነን። ለአስተባባዮች ሁሉ በዚያን ቀን ወዮውላቸው።

أَلَمْ نَجْعَلِ ٱلْأَرْضَ كِفَاتًا ﴿٢٥﴾ أَحْيَآءً وَأَمْوَٰتًا ﴿٢٦﴾ وَجَعَلْنَا فِيهَا رَوَٰسِىَ شَٰمِخَٰتٍ
وَأَسْقَيْنَٰكُم مَّآءً فُرَاتًا ﴿٢٧﴾ وَيْلٌ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ ﴿٢٨﴾

**25-28.** (ሰዎች ሆይ!) ምድርን ሰብሳቢ አላደረግናትምን?። ህያው ሆናችሁም ሙታን ሆናችሁ። በውስጧም ከፍተኛዎችን (ትላልቅ) ተራራዎች አደረግን፤ ጣፋጭ ውሃንም አጠጣናችሁ። ለአስተባባች በዚያ ቀን ወዮላችሁ።

ٱنطَلِقُوٓا۟ إِلَىٰ مَا كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ﴿٢٩﴾ ٱنطَلِقُوٓا۟ إِلَىٰ ظِلٍّ ذِى ثَلَٰثِ شُعَبٍ ﴿٣٠﴾
لَّا ظَلِيلٍ وَلَا يُغْنِى مِنَ ٱللَّهَبِ ﴿٣١﴾ إِنَّهَا تَرْمِى بِشَرَرٍ كَٱلْقَصْرِ ﴿٣٢﴾ كَأَنَّهُۥ جِمَٰلَتٌ
صُفْرٌ ﴿٣٣﴾ وَيْلٌ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ ﴿٣٤﴾

**29-34.** ወደ እዚያ በእርሱ ታስተባብሉ ወደ ነበራችሁት ቅጣት ሂዱ። ባለ ሶስት ቅርንጫፎች ወደ ሆነው ጥላ (ሂዱ)። ጥላም ያልሆነ ከእሳቱም ላንቃ የማያድን ወደ ሆነው ሂዱ። እርሷ እንደ ታላላቅ ህንፃ የሆኑን ቃንቄዎች (የእሳት ፍንጣሪዎች) ትወረውራለች። ቃንቄውም ልክ ዳለቻዎች ግመሎችን ይመስላል። ለአስተባባዩች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮላቸው።

هَٰذَا يَوْمُ لَا يَنطِقُونَ ﴿٣٥﴾ وَلَا يُؤْذَنُ لَهُمْ فَيَعْتَذِرُونَ ﴿٣٦﴾ وَيْلٌ يَوْمَئِذٍ لِّلْمُكَذِّبِينَ ﴿٣٧﴾

**35-37.** ይህ የማያናገሩበት ቀን ነው። ይቅርታም ይጠይቁ ዘንድ አይፈቀድላቸውም። ለአስተባባዮች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮውላቸው።

هَٰذَا يَوۡمُ ٱلۡفَصۡلِۖ جَمَعۡنَٰكُمۡ وَٱلۡأَوَّلِينَ ﴿٣٨﴾ فَإِن كَانَ لَكُمۡ كَيۡدٞ فَكِيدُونِ ﴿٣٩﴾
وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ﴿٤٠﴾

**38-40.** ይህ የመለያው ቀን ነው። እናንተንም የፊተኞችንም ሰበሰብናችሁ። ለእናንተም ለማምለጥ ብልሃት እንዳላችሁ ተተናኮሉኝ። ለአስተባባዩች ሁሉ በዚያ ቀን ወዬውላቸው።

إِنَّ ٱلۡمُتَّقِينَ فِي ظِلَٰلٖ وَعُيُونٖ ﴿٤١﴾ وَفَوَٰكِهَ مِمَّا يَشۡتَهُونَ ﴿٤٢﴾ كُلُواْ وَٱشۡرَبُواْ هَنِيٓـَٔۢا بِمَا كُنتُمۡ
تَعۡمَلُونَ ﴿٤٣﴾ إِنَّا كَذَٰلِكَ نَجۡزِي ٱلۡمُحۡسِنِينَ ﴿٤٤﴾ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ﴿٤٥﴾

**41-45.** ጥንቅቆች በጥላዎችን በምንጮችና በሚፈልጉትም የፍራፍሬ አይነቶች ውስጥ ናቸው። ትሰሩትም በነበራችሁት ዋጋ የምትደሰቱ ሆናችሁ ብሉ፤ ጠጡም ይባላሉ፤ እኛ እንደዚሁ መልካም ሰሪዎች ሁሉ እንመነዳለን፤ ለአስተባባዮች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮውላቸው።

كُلُواْ وَتَمَتَّعُواْ قَلِيلًا إِنَّكُم مُّجۡرِمُونَ ﴿٤٦﴾ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ﴿٤٧﴾

**46-47.** (እናንተ ከሐዲያን ሆይ!) ብሉ ጥቂትንም ጊዜ ተጠቀሙ እናንተ አመፀኞች ናችሁና። ለአስተባባዮች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮውላቸው።

وَإِذَا قِيلَ لَهُمُ ٱرۡكَعُواْ لَا يَرۡكَعُونَ ﴿٤٨﴾ وَيۡلٞ يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ﴿٤٩﴾
فَبِأَيِّ حَدِيثِۭ بَعۡدَهُۥ يُؤۡمِنُونَ ﴿٥٠﴾

**48-50.** ለእነርሱ ስገዱም በተባሉ ጊዜ አይሰግዱም።* ለአስተባባዩች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮውላቸው። ከእርሱም ሌላ በየትኛው ንግግር ያምናሉ?

✷ (ሀ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- «ሰዎች ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም» እስከሚሉ እኛ የምንሰግደው አይነት ሶላት እስኪደግሱ፤ እኛ ፊታችንን ወደምናዞርበት እስኪያዞሩ እኛ እንደምናርደው እስከ ሚያርዱ ድረስ እንድጋደላቸው ታዝዣለሁ። ይህን ከፈፀሙ ደማቸውና ንብረታቸው በኛ ዘንድ የተጠበቀ ነው። በሕጋዊ መንገድ ካልሆነ በስተቀር በነርሱ ውስጥ ጣልቃ አንገባም። ስለ ሂሳባቸው ያለው ግንኙነት ከአላህ ጋር ይሆናል።

(ለ) የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዲህ ብለዋል፡- «ሰዎች አዛን በማለትና ሶላት ወቅቶች በመጀመሪያ ረድፍ የመገኘትን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እና ያንን ምንዳ ለማግኘት ምልክት ከማስቀመጥ በስተቀር ሌላ አማራጭ ባይኖር ምልክቱን ከማስቀመጥ ወደኋላ አይሉም ነበር። የዙህርን ሶላት በወቅቱ የመስገድን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ ደግሞ በወቅቱ ቀድመው

ለመገኘት እርስ በርሳቸው በተሽቀዳደሙ ነበር። እንዲሁም የዒሻንና የፈጅርን ሶላቶችን በጀመዓ መስጅድ ተገኝተው የመስገድን ምንዳ ቢያውቁ ኖሮ እነዚህን ሶላቾች ለመስገድ እየተሳቡም ቢሆን ይመጡ ነበር»

**ከተላኪዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-50) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙቶ መነሳትን በመሀላ አጠንክሮ ማረጋገጥ፤
2. ፍጡሮች ከአላህ ሌላ በሆነ አካል መማል ክልክል ቢሆንም አላህ ግን በፈለገው መማል የሚችል መሆኑን በመላኢኮችና በነፍሳት በመማል መግለፁን፤
3. ሙቶ መነሳት እንዳለ ለማሳመን ብዙ ማስረጃዎች እንዳሉ፤
4. አላህ በፍጡሮቹ ላይ የዋለውን ከፍተኛ ውለታ በግልፅ ማሳየት፤
5. ብዙ ሰዎች አላህን የሚያመሰግኑ መሆኑን፤
6. ለከሓዲያን የተገባው ዛቻ አስፈሪ መሆኑን፤
7. በገሀነም ቅጣት ክብደትና ክፋት መገረም፤
8. የቂያማ ቀን ጭንቅ ብርቱ ስለመሆኑ፤
9. የክህደት ቁንጮ በአላህ ማስተባበል ስለመሆኑ፤
10. የቁርኣን ዘገባ እውነተኛነት ለመካ ከሓዲያን የዛተው ዛቻ በአጭር ጊዜ ሲፈፀም መታየቱ በቂ ስለ መሆኑ፤
11. መስጊድ ሲገባ ሰዎች እየሰገዱ ያገኘ ሰው ያለ ምን ጥያቄ እነሱ ጋር አብሮ መስገድ እንዳለበት እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የተላላኪዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

ምዕራፍ (78)

## የዜናው ምዕራፍ

(ሱረቱ አንነበእ)

سُورَةُ النَّبَإِ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (40) ናቸው።**

**የሱረቱ አን-ነበእ መግቢያ**

ይህ ምዕራፍ ሱረቱል ዐምመ ሱረቱል የተሳአሉን፤ ሱረቱል አል ሙዕሲሳራት በመባልም ይታወቃል። ቁርኣንና አስተምሮቱን በተመለከተ የመካ ሰወች የፈጠሩትን ቅጥፈት አውስቶ የሙቶ መነሳትን ሀቅነት አረጋግጦ በሱ የሚጠራጠሩትን አስፈራርቶ ሙቶ መነሳት በአላህ ዘንድ ቀላል ለመሆኑ ብዙ ማስረጃዎች አቅርቦ ምልክቶቹንም በዝርዝር አውስቷል። በመቀጠልም የአመፀኞችን መጨረሻና የፈርሀያኖችን ልማዶች በዝርዝር አስተምሮ ይህን አስፈራሪ ቀን በማስጠንቀቅ በማስፈራራት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

በቁርኣን ውስጥ ካሉ ሳይንሳዊ ተዓምራት ስለተራራዎች የተነገረው ሚስጥር ነው። እሱም ዛሬ ሳይንቲስቶች በዝርዝር ያስቀመጡትን ከ (1420) አመት በፊት ማውሳቱ ይህ ቁርኣን ከአላህ የመጣ እንጂ የሰው ልጆች ስራ አለመሆኑን ያመለክታል። ተራራዎች ወደ መሬት ውስጥ የጠለቁ ስሮች እንዳሏቸውና ለምድረ ገፅ መረጋጋትና ሚዛን መጠበቅ አስተዋፅኦ እንዳላቸው ሳይንስ በቅርቡ በ (1865) ሮያል ሰር ጆርጅ አር የተባለው ሳይንቲስት Earth Press and Siever በተሰኘው መፅሐፍ ገፅ (435) ለመጀመሪያ ጊዜ እንደገለፀው ደረስኩበት ያለው ሀቅ ገና ሳይንቲስት ባልታወቀበት ዘመን የተገለፀው ቁርኣን ቀድሞ አስቀምጦት ይገኛል። አል-ነበአ (6-7) እና አል-ነህል (15) ላይ። ይኸው ሳይንቲስት በዚሁ መፅሐፉ በቅፅ (5) በገፅ (44-45) ባለው ቁርኣን ስለ ተራራ ያወሳውን ይዘረዝራል። ይህም ለከሃዲያን ቁርኣን ከአላህ ለመሆኑ ማረጋገጫ ነው

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

عَمَّ يَتَسَآءَلُونَ ١ عَنِ ٱلنَّبَإِ ٱلۡعَظِيمِ ٢ ٱلَّذِي هُمۡ فِيهِ مُخۡتَلِفُونَ ٣
كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٤ ثُمَّ كَلَّا سَيَعۡلَمُونَ ٥

**1-5.** ከምን ነገር ይጠያየቃሉ? ስለዚያ እነርሱ በእርሱ ላይ በተለያዩበትና በተወዛገቡበት በታላቁ ዜና (ከቁርአን ይጠያየቃሉ)። ጉዳዩ እነርሱ እንደሚሉት አይደለም። ትክክለኛውን ወደ ፊት ያውቃሉ። ከዚያ በዚህ ጉዳይ ትክክለኛውን ወደ ፊት ያውቃሉ።

أَلَمۡ نَجۡعَلِ ٱلۡأَرۡضَ مِهَٰدٗا ٦ وَٱلۡجِبَالَ أَوۡتَادٗا ٧ وَخَلَقۡنَٰكُمۡ أَزۡوَٰجٗا ٨
وَجَعَلۡنَا نَوۡمَكُمۡ سُبَاتٗا ٩ وَجَعَلۡنَا ٱلَّيۡلَ لِبَاسٗا ١٠ وَجَعَلۡنَا ٱلنَّهَارَ مَعَاشٗا ١١

**6-11.** ምድርን እንደ ምንጣፍ የምትመች አላደርግንምን? መሬት እንዳያረገርግ ጋራዎችን ችካሎች አድርገናል። (ሰዎች ሆይ)፣ ብዙ ዓይነቶች አድርገን ፈጠርናችሁ። እንቅልፋችሁን እረፍት አደረግን። ሌሊቱንም ልባስ አደረግን። ቀኑንም ለኑሮ መስሪያ፣ (ለጉዳይ መከወኛ) አደረግን።

وَبَنَيْنَا فَوْقَكُمْ سَبْعًا شِدَادًا ﴿١٢﴾ وَجَعَلْنَا سِرَاجًا وَهَّاجًا ﴿١٣﴾ وَأَنزَلْنَا مِنَ ٱلْمُعْصِرَٰتِ مَآءً ثَجَّاجًا ﴿١٤﴾ لِّنُخْرِجَ بِهِۦ حَبًّا وَنَبَاتًا ﴿١٥﴾ وَجَنَّٰتٍ أَلْفَافًا ﴿١٦﴾

**12-16.** ከበላያቸሁም ሰባትን ብርቱዎች (ሰማያት) ገነባን። አንፀባራቂ ብርሃንንም ፀሐይን አደርግንላችሁ። ከአረገዙት ደመናዎችም በእርሱ እህልና ቅጠላ ቅጠልን፣ የተቆላለፉ አትክልቶችንም እናመጣ ዘንድ የሚንቧቧ ውሃን አደረግን።

إِنَّ يَوْمَ ٱلْفَصْلِ كَانَ مِيقَٰتًا ﴿١٧﴾ يَوْمَ يُنفَخُ فِى ٱلصُّورِ فَتَأْتُونَ أَفْوَاجًا ﴿١٨﴾ وَفُتِحَتِ ٱلسَّمَآءُ فَكَانَتْ أَبْوَٰبًا ﴿١٩﴾ وَسُيِّرَتِ ٱلْجِبَالُ فَكَانَتْ سَرَابًا ﴿٢٠﴾

**17-20.** በህዝቦች መካከል የመለያው ቀን የተወሰነ ጊዜ ነው። ይህ የሚሆነው በቀንዱ የሚነፋበትና የተለያዩ ጭፍሮች ሆናችሁ በምትመጡ ቀን ነው። ሰማይም በምትከፈትና ባለ ብዙ ደጃፎችም በምትሆንበት ቀን። ጋራዎችም የሚናዱበትና እንደ ሲሪብዶም የሚሆንበት ቀን ነው።

إِنَّ جَهَنَّمَ كَانَتْ مِرْصَادًا ﴿٢١﴾ لِّلطَّٰغِينَ مَـَٔابًا ﴿٢٢﴾ لَّٰبِثِينَ فِيهَآ أَحْقَابًا ﴿٢٣﴾ لَّا يَذُوقُونَ فِيهَا بَرْدًا وَلَا شَرَابًا ﴿٢٤﴾ إِلَّا حَمِيمًا وَغَسَّاقًا ﴿٢٥﴾ جَزَآءً وِفَاقًا ﴿٢٦﴾

**21-26.** ገሀነም (ለከሓዲያን) መጠባበቂያ ኬላ (ስፍራ) ናት። ለህግ ለወሰን ተላላፊዎች መመላለሻ ስትሆን። በውስጧ ብዙ ዘመናትን ነዋሪዎች ሲሆኑ፣ ሙቅ የፈላን ውሃንና እዥን እንጂ በውስጧ (ቅዝቃዜንም መጠጥንም) አይቀምሱም አያገኙም። ተስማሚን ፍትሃዊን (ተመጣጣኝን) ምንዳ ይመነዳሉ።

إِنَّهُمْ كَانُوا۟ لَا يَرْجُونَ حِسَابًا ﴿٢٧﴾

**27.** እነርሱ ምርመራን የማይፈሩ ነበሩና። ተጠያቂ እንደሚሆኑ ቅንጣት አይጠብቁም ነበርና።

وَكَذَّبُواْ بِـَٔايَٰتِنَا كِذَّابٗا ﴿٢٨﴾ وَكُلَّ شَيۡءٍ أَحۡصَيۡنَٰهُ كِتَٰبٗا ﴿٢٩﴾ فَذُوقُواْ فَلَن نَّزِيدَكُمۡ إِلَّا عَذَابًا ﴿٣٠﴾

**28-30.** በአንቀፆቻችን ማስተባበልን አስተባበሉና፡፡ ነገሩን ሁሉ በመዝገብ ውስጥ የተፃፈ ሲሆን አጠቃለልነው፡፡ (የተግባራችሁን ውጤት) ቅመሱም፤ ቅጣትንም እንጂ ሌላን አንጨምርላችሁም (ይባላሉ)፡፡

إِنَّ لِلۡمُتَّقِينَ مَفَازًا ﴿٣١﴾ حَدَآئِقَ وَأَعۡنَٰبٗا ﴿٣٢﴾ وَكَوَاعِبَ أَتۡرَابٗا ﴿٣٣﴾ وَكَأۡسٗا دِهَاقٗا ﴿٣٤﴾
لَّا يَسۡمَعُونَ فِيهَا لَغۡوٗا وَلَا كِذَّٰبٗا ﴿٣٥﴾ جَزَآءٗ مِّن رَّبِّكَ عَطَآءً حِسَابٗا ﴿٣٦﴾ رَّبِّ ٱلسَّمَٰوَٰتِ
وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا بَيۡنَهُمَا ٱلرَّحۡمَٰنِۖ لَا يَمۡلِكُونَ مِنۡهُ خِطَابٗا ﴿٣٧﴾

**31-37.** ለጥንቅቆቹ (አላህን ለሚፈሩ) መዳኛ ስፍራ አላቸው፡፡ አትክልቶችንና ወይኖችም፡፡ በእድሜ እኩያዎች የሆኑ ጡተ ጡተ ጉቻማዎችም፡፡ በወይን ጠጅ የተሞሉ ብርጭቆዎችም፡፡ በውስጧ ትርፍ ቃልንም፤ ማስዋሸትንም አይሰሙም፡፡ ከጌታህ የሆነን ምንዳ፤ በቂ ስጦታን ተሰጡ፡፡ የሰማያትና የምድር በመካከላቸውም ያለው ሁሉ ጌታና በጣም አዛኝ ከሆነው ተመነዱ፤ ከእርሱ ጋር መነጋገርን አይችሉም፡፡

يَوۡمَ يَقُومُ ٱلرُّوحُ وَٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ صَفّٗاۖ لَّا يَتَكَلَّمُونَ إِلَّا مَنۡ أَذِنَ لَهُ ٱلرَّحۡمَٰنُ وَقَالَ صَوَابٗا ﴿٣٨﴾
ذَٰلِكَ ٱلۡيَوۡمُ ٱلۡحَقُّۖ فَمَن شَآءَ ٱتَّخَذَ إِلَىٰ رَبِّهِۦ مَـَٔابًا ﴿٣٩﴾

**38-39.** መላኩ (ጅብሪል) እና ሌሎች መላዕክትም የተሰለፉ ሆነው በሚቆሙበት ቀን አረህማን ለእርሱ የፈቀደለትና ትክክለኛን ቃል* ያለ ሰው ብቻ ቢሆን እንጂ መነጋገርን አይችሉም፡፡ ያ፣ መከሰቱም የተረጋገጠ ቀን ነው፡፡ የፈለገ ሰው ወደ ጌታው በመልካም ተግባር መመለስን ተግባሩ አድርጎ ይይዛል፡፡

* እውነትን የተናገረ ማለት ሲሆን የእውነቶች ሁሉ «እውነት ቃል ላኢላሀ ኢለላህ» ከአላህ በስተቀር ሊመለክ የሚገባው ማንም የለም የሚለው ነው፡፡

إِنَّآ أَنذَرۡنَٰكُمۡ عَذَابٗا قَرِيبٗا يَوۡمَ يَنظُرُ ٱلۡمَرۡءُ مَا قَدَّمَتۡ يَدَاهُ
وَيَقُولُ ٱلۡكَافِرُ يَٰلَيۡتَنِي كُنتُ تُرَٰبَۢا ﴿٤٠﴾

**40.** እኛ ሰዎች ሁሉ በሁለት እጆቻቸው ያስቀደሙትን በግልፅ የሚያይበትና ከሓዲያን ሁሉ ዋ ምኞቴ ምንነው አፈር በሆንኩ ባልተቀሰቀስኩኝ በሚሉበት ቀን ቅርብ የሆነን ቅጣት አስጠነቀቅናችሁ፡፡

**ከዜናው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-40) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ ተዐምሮችን ለማስተዋል ግፊት ማሳደር፤
2. ሰዎች እየተጨቃጨቁበት የነበረውን የቂያማ እለት አይቀሬ መሆኑን ማረጋገጥ፤
3. ዛሬ ሰዎች እየተጠራጠሩ ያለው የቂያማ ቀን ጉዳይ ሰው ልጆች ከሞቱበት ዕለት ጀምሮ የሚያረጋጡበት ጉዳይ መሆኑን፤
4. ግፈኝነት በግልፅ ማውገዝ፤
5. የሰው ልጆች ተግባር ደግም ይሁን መጥፎ የሚመዘገብ መሆኑን፤
6. የቂያመ ቀን ቅጣት ለከሓዲያን ዘላለማዊ መሆኑን፤
7. የፈሪሀያንን ክብርና ደረጃ ምን እንደሆነ ማሳወቅ፤
8. ስለጀነት አጠር ያለችና ውብ የሆነች ማብራሪያና አጓጊ መግለጫ፤
9. ውሸትና አሉባልታ ንግግር አስቀያሚነታቸውን በግልፅ ማስረዳት፤
10. የቂያማ ሁኔታዎች በጣም ከባድ እንደሆኑና ያስተባበሉት ሁሉ የሚጠብቃቸው አጅግ አስከፊ ቅጣት እንደሆነ፤
11. መልካም ስራዎችን እንዲሰሩ ግፊት ማሳደርና ከመጥፎ ተግባራት ሁሉ እንዲታቀቡ ማስጠንቀቅ፤
12. በአላህ ፊት መናገር መላኢኮች እንኳን ቢሆኑ ያለ ፈቃዱ እንደማይችሉ፤
13. የሰዎች ተግባር እያንዳንዷ ብታንስም እንደምትመዘገብ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የዜናው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (79)
## የአውጪዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አን-ናዚዓት)

سُورَةُ النَّازِعَاتِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (46) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلنَّٰزِعَٰتِ غَرۡقٗا ١ وَٱلنَّٰشِطَٰتِ نَشۡطٗا ٢ وَٱلسَّٰبِحَٰتِ سَبۡحٗا ٣
فَٱلسَّٰبِقَٰتِ سَبۡقٗا ٤ فَٱلۡمُدَبِّرَٰتِ أَمۡرٗا ٥ يَوۡمَ تَرۡجُفُ ٱلرَّاجِفَةُ ٦ تَتۡبَعُهَا ٱلرَّادِفَةُ ٧
قُلُوبٞ يَوۡمَئِذٖ وَاجِفَةٌ ٨ أَبۡصَٰرُهَا خَٰشِعَةٞ ٩

**1-9.** ነፍስን (ሩህን) በኃይል አውጪዎች በሆኑት፤ በቀስታ መምዘዝን መዛዦች በሆኑት፤ መዋኘትንም ዋኚዎች በሆኑት፤ መቅደምንም ቀዳሚዎች በሆኑት፤ ነገርንም አስተናባሪዎች በሆኑት መላዕክት እምላለሁ። (በእርግጥ ትቀሰቀሳላችሁ)። ተርገፍጋፊይቱ ምድር በምትርገፈገፍበት ቀን፤ ተከታይቱ የምትከተላት ስትሆን (ትቀሰቀሳላችሁ)። በዚያ ቀን ልቦች ተሸባሪዎች ናቸው። ዓይኖቻቸው ተዋራጆች አቀርቃሪዎች ናቸው።

يَقُولُونَ أَءِنَّا لَمَرۡدُودُونَ فِي ٱلۡحَافِرَةِ ١٠ أَءِذَا كُنَّا عِظَٰمٗا نَّخِرَةٗ ١١ قَالُواْ تِلۡكَ إِذٗا كَرَّةٌ
خَاسِرَةٞ ١٢ فَإِنَّمَا هِيَ زَجۡرَةٞ وَٰحِدَةٞ ١٣ فَإِذَا هُم بِٱلسَّاهِرَةِ ١٤

**10-14.** እኛ ወደ መጀመሪያይቱ ሁኔታ ተመላሾች ነን እንዴ? ይላሉ። የበሰበሱ አጥንቶች በሆንን ጊዜ እንደገና እንቀሰቀሳለን? ያን ጊዜማ የከሳራ መመለስ ነው ይላሉ። እርሷን ለማድረግ አንዲት ጩኸት ብቻ ናት። ወዲያውኑ እንቅልፍ በሌለባት ቦታ ላይ ይሆናሉ።

هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ مُوسَىٰٓ ١٥ إِذۡ نَادَىٰهُ رَبُّهُۥ بِٱلۡوَادِ ٱلۡمُقَدَّسِ طُوًى ١٦ ٱذۡهَبۡ إِلَىٰ فِرۡعَوۡنَ
إِنَّهُۥ طَغَىٰ ١٧ فَقُلۡ هَل لَّكَ إِلَىٰٓ أَن تَزَكَّىٰ ١٨ وَأَهۡدِيَكَ إِلَىٰ رَبِّكَ فَتَخۡشَىٰ ١٩ فَأَرَىٰهُ ٱلۡأٓيَةَ

ٱلۡكُبۡرَىٰ ٢٠ فَكَذَّبَ وَعَصَىٰ ٢١ ثُمَّ أَدۡبَرَ يَسۡعَىٰ ٢٢ فَحَشَرَ فَنَادَىٰ ٢٣ فَقَالَ أَنَا۠ رَبُّكُمُ
ٱلۡأَعۡلَىٰ ٢٤ فَأَخَذَهُ ٱللَّهُ نَكَالَ ٱلۡأٓخِرَةِ وَٱلۡأُولَىٰٓ ٢٥ إِنَّ فِي ذَٰلِكَ لَعِبۡرَةٗ لِّمَن يَخۡشَىٰٓ ٢٦

**15-26.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሙሳ ወሬ መጣልህን? ጌታው በተቀደሰው በጡዋ ሸለቆ በጠራው ጊዜ፤ ወደ ፈርዖን ሂድ፤ እርሱ ወሰን አልፏልና። እራስህን ለማጥራት ትመኛለህን? በለውም። ጌታህን ትፈራ ዘንድ መንገዱን ልመራህ፤ (መንገድ አለህን?) አለው። ሙሳ ለፈርዖን ታላቁንም ተዐምር አሳየው። ፈርዖንም ሙሳን አስተባበለም፤ (አመፀም)። ከዚያ ለመጥፋት የሚተጋ ሆኖ ዞረ። ሰራዊቶችም ሰበሰበም ተጣራም። እኔ ታላቁ ጌታችሁ ነኝ አለም። አላህም በኋለኛይቱና በፊተኛይቱ ቃል ቅጣት ያዘው። በዚህ ውስጥ አላህን ለሚፈሩ ሰው ሁሉ በእርግጥ መገምገሚያና ማስጠንቀቂያ አለበት።

ءَأَنتُمۡ أَشَدُّ خَلۡقًا أَمِ ٱلسَّمَآءُۚ بَنَىٰهَا ٢٧ رَفَعَ سَمۡكَهَا فَسَوَّىٰهَا ٢٨ وَأَغۡطَشَ لَيۡلَهَا وَأَخۡرَجَ
ضُحَىٰهَا ٢٩ وَٱلۡأَرۡضَ بَعۡدَ ذَٰلِكَ دَحَىٰهَآ ٣٠ أَخۡرَجَ مِنۡهَا مَآءَهَا وَمَرۡعَىٰهَا ٣١ وَٱلۡجِبَالَ
أَرۡسَىٰهَا ٣٢ مَتَٰعٗا لَّكُمۡ وَلِأَنۡعَٰمِكُمۡ ٣٣

**27-33.** በአፈጣጠር እናንተ ይበልጥ የበረታችሁ ናችሁን? ወይስ ሰማይ? (አላህ) ገነባት። ከፍታዋን አጎነ አስተካከላትም። ሌሊቷንም አጨለመ ቀኗንም ግልፅ አደረገ። ምድርንም ከዚህ በኋላ ዘረጋት። ውሃዋንና ግጦሿን ከእርሷ አወጣ። ጋራዎችንም አደላደላቸው። (ቸከላቸው)። ለእናንተም ለእንስሶቻችሁም መጣቀሚያ ናት። (ይሄን አደረገ)

فَإِذَا جَآءَتِ ٱلطَّآمَّةُ ٱلۡكُبۡرَىٰ ٣٤ يَوۡمَ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ مَا سَعَىٰ ٣٥ وَبُرِّزَتِ ٱلۡجَحِيمُ لِمَن
يَرَىٰ ٣٦ فَأَمَّا مَن طَغَىٰ ٣٧ وَءَاثَرَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ٣٨ فَإِنَّ ٱلۡجَحِيمَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ٣٩ وَأَمَّا
مَنۡ خَافَ مَقَامَ رَبِّهِۦ وَنَهَى ٱلنَّفۡسَ عَنِ ٱلۡهَوَىٰ ٤٠ فَإِنَّ ٱلۡجَنَّةَ هِيَ ٱلۡمَأۡوَىٰ ٤١

**34-41.** ታላቂቱም መዓት በመጣች ጊዜ፤ ሰው ሁሉ የሰራውን የሚያስታውስበት ቀን፤ ገሀነምም ለሚያይ ሰው በተገለጠች ጊዜ፤ የካደ ሰውማ፤ ቅርቢቱንም ሕይወት የመረጠ፤ በእርግጥ ጀሀነም መኖሪያው ናት። በጌታው ፊት መቆምን የፈራና ነፍሱንም ከዝንባሌዋ የከለከለ ሰውማ፤ በእርግጥ ገነት መኖሪያው ናት።

يَسْـَٔلُونَكَ عَنِ ٱلسَّاعَةِ أَيَّانَ مُرْسَىٰهَا ﴿٤٢﴾ فِيمَ أَنتَ مِن ذِكْرَىٰهَآ ﴿٤٣﴾
إِلَىٰ رَبِّكَ مُنتَهَىٰهَآ ﴿٤٤﴾ إِنَّمَآ أَنتَ مُنذِرُ مَن يَخْشَىٰهَا ﴿٤٥﴾

**42-45.** ከሞት መነሻዋ ሰዓት መቼም እንደምትከሰት ይጠይቁሃል፡፡ ለመሆኑ አንተ ስለዚያች እለት ምን እውቀት ይኖርሃል? የእርሷ ጉዳይ የሚመለሰው ወደ ጌታህ ብቻ ነው፡፡ አንተ ያለብህ ለሚፈራት ሰው ሁሉ ስለ እርሷ ከወዲሁ ማስጠንቀቅ ብቻ ነው፡፡

كَأَنَّهُمْ يَوْمَ يَرَوْنَهَا لَمْ يَلْبَثُوٓا۟ إِلَّا عَشِيَّةً أَوْ ضُحَىٰهَا ﴿٤٦﴾

**46.** እነርሱ የሚያይዋት ቀን የአንዲትን ቀን ምሽት ወይም ረፋዷን እንጂ ያልቆዩ ይመስላሉ፡፡

**ከነፍስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-46) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ በፈለገው ነገር መማል የሚችል መሆኑን፤
2. የትክክለኛ አማኞች ሩህ በቀላሉ እንደምትወጣና የከሓዲያን ግን ከፍተኛ ጭነቀት እንደሚጠብቃት፤
3. ሙቶ መነሳት የማይቀር ሀቅ መሆኑን በመሀላ ማረጋገጥ፤
4. አስተማሪ መታገስ እንዳለበት ማፅናናት
5. ነቢዩ ሙሳ ጌታቸዉን በግልፅ እንዳናገሩት፤
6. ማንም ሰው መንፈሱን ማፅዳት የሚችለው በኢስላም ብቻ መሆኑን፤
7. አላህን በትክክል መፍራት የሚችለው አላህን በትክክል የሚያውቀው መሆኑን፤
8. ተዐምርን ማየት ማመንን ላያስከትል እንደሚችል፤
9. ራሱን እንደ አምላክ ቆጥሮ ሰዎች እንዲገዙት ማዘዝ ምን ያክል አስከፊ ተግባር መሆኑን፤
10. አላህ ለሰዎች ብዙ ፀጋዎችን እንደዋለላቸው መግለፅ፤
11. ከፍተኛን ነገር በማውሳት ለአነስተኛው ማስረጃ ማድረግ፤ ብዙን ነገር በማውሳት ለጥቂቱ ማስረጃ መጥቀስ እንደሚገባ፤
12. ሰዎች በተነሳኤ ዕለት ሁለት አይነት እንደሚሆኑ፤
13. የተንሳኤ ቀን መቸ እንደሚከሰት የሚያቀው አንድ አላህ ብቻ መሆኑን፤
14. የተንሳኤ ቀን ቅጣቶች፤ ፈተናዎች አንዱ ሌላዉን እንደሚያስረሳ እንማራለን፡፡

በአላህ ፈቃድ የአውጪዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ፡፡

# ምዕራፍ (80)
# የማጨፍገግ ምዕራፍ
## (ሱረቱ ዐበሰ)

سُورَةُ عَبَسَ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (42) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

عَبَسَ وَتَوَلَّىٰٓ ۝١ أَن جَآءَهُ ٱلۡأَعۡمَىٰ ۝٢ وَمَا يُدۡرِيكَ لَعَلَّهُۥ يَزَّكَّىٰٓ ۝٣
أَوۡ يَذَّكَّرُ فَتَنفَعَهُ ٱلذِّكۡرَىٰٓ ۝٤

**1-4.** ዓይነስውሩ ወደ እርሱ ስለመጣ። (ሙሐመድ) ፊቱን አጨፈገገና ዞረም፤ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምን ያሳውቅሃል? ምንአልባትም (ይህ አይነስውር ሰው ከአንተ በሚሰማው ምክር ከኃጢአቶቹ) ሊጥራራ ይከጀላል። ወይም ሊገሰፅና ግሳጼይቱም ልትጠቅመው ይከጀላል።

ከማጨፍገግ ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አብደላህ ቢን ኡሚ መክቱም የተባሉ አይነ ስውር ሱሃብይ ለመማር ጓጉተው ወደ ነብዩ ሲመጡ ነብዩ (ﷺ) የመካ ታላላቅ ባላባቶችን ያነጋግሩ ስለነበር ለጊዜው እሱን ማናገር ባለመፈለጋቸውና ፊታቸውን በማዞረቸው ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

أَمَّا مَنِ ٱسۡتَغۡنَىٰ ۝٥ فَأَنتَ لَهُۥ تَصَدَّىٰ ۝٦ وَمَا عَلَيۡكَ أَلَّا يَزَّكَّىٰ ۝٧
وَأَمَّا مَن جَآءَكَ يَسۡعَىٰ ۝٨ وَهُوَ يَخۡشَىٰ ۝٩ فَأَنتَ عَنۡهُ تَلَهَّىٰ ۝١٠

**5-10.** ያ! ከአላህ የተብቃቃውን ሰውማ፤ አንተ ለእርሱ (ለእምነተ ቢሱ) ትዘጋጃለህ። ባይጥራራና (ባያምን)፤ በአንተ ላይ ምንም የሌለብህ ስትሆን፤ ያ እየገሰገሰ የመጣው ሰው፤ እርሱ አላህን የሚፈራ ሲሆን፤ አንተ ከእርሱ ትዘናጋለህ።

كَلَّآ إِنَّهَا تَذۡكِرَةٞ ۝١١ فَمَن شَآءَ ذَكَرَهُۥ ۝١٢ فِي صُحُفٖ مُّكَرَّمَةٖ ۝١٣ مَّرۡفُوعَةٖ مُّطَهَّرَةِۭ ۝١٤
بِأَيۡدِي سَفَرَةٖ ۝١٥ كِرَامِۭ بَرَرَةٖ ۝١٦

**11-16.** ተከልከል፤ እርሷ ማስገንዘቢያ ናት፡፡ የፈለገ ሰው (ቁርኣኑን) ያስታውሰዋል፡፡ በተከበሩት ፅሑፎች ውስጥ ነው፡፡ ከፍ በተደረገና፤ በንፁሁ ፅሑፍ ውስጥ ነው፡፡ በፀሐፊዎች መላዕክት እጆች (ንፁህ የተደረገ)፡፡ የተከበሩና ታዛዦች በሆኑት ፀሐፊዎች (እጆች)፤ ነው፡፡

قُتِلَ ٱلۡإِنسَٰنُ مَآ أَكۡفَرَهُۥ ﴿١٧﴾ مِنۡ أَيِّ شَيۡءٍ خَلَقَهُۥ ﴿١٨﴾ مِن نُّطۡفَةٍ خَلَقَهُۥ فَقَدَّرَهُۥ ﴿١٩﴾

**17-19.** ሰው ተረገመ፡፡ ምን ከሓዲ አደረገው፡፡ (ጌታው) ከምን ነገር ፈጠረው? (አያስብምን?) ከፍትወት ጠብታ ፈጠረው፤ መጠነውም፡፡

ከማጨፍገግ ምዕራፍ (17) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ሱረቱ አን-ነጅም በወረደ ጊዜ ኡትበት ኢብኑ አቢለህብ በነጅም ጌታ እክዳለሁ በማለቱ ነው፡፡ (ሱዩጢ)

ثُمَّ ٱلسَّبِيلَ يَسَّرَهُۥ ﴿٢٠﴾ ثُمَّ أَمَاتَهُۥ فَأَقۡبَرَهُۥ ﴿٢١﴾ ثُمَّ إِذَا شَآءَ أَنشَرَهُۥ ﴿٢٢﴾ كَلَّا لَمَّا يَقۡضِ مَآ أَمَرَهُۥ ﴿٢٣﴾

**20-23.** ከዚያም (መውጫ) መንገዱን አገራው፡፡ ከዚያም ገደለው፡፡ እንዲቀበርም አደረገው፤ ከዚያ ማንሳቱን በፈለገ ጊዜ ያስነሳዋል፡፡ በእውነት ያንን ጌታው ያዘዘውን ገና አልፈፀመም፡፡

فَلۡيَنظُرِ ٱلۡإِنسَٰنُ إِلَىٰ طَعَامِهِۦٓ ﴿٢٤﴾ أَنَّا صَبَبۡنَا ٱلۡمَآءَ صَبّٗا ﴿٢٥﴾ ثُمَّ شَقَقۡنَا ٱلۡأَرۡضَ شَقّٗا ﴿٢٦﴾
فَأَنۢبَتۡنَا فِيهَا حَبّٗا ﴿٢٧﴾ وَعِنَبٗا وَقَضۡبٗا ﴿٢٨﴾ وَزَيۡتُونٗا وَنَخۡلٗا ﴿٢٩﴾ وَحَدَآئِقَ غُلۡبٗا ﴿٣٠﴾ وَفَٰكِهَةٗ
وَأَبّٗا ﴿٣١﴾ مَّتَٰعٗا لَّكُمۡ وَلِأَنۡعَٰمِكُمۡ ﴿٣٢﴾

**24-32.** ሰው ወደ ምግቡ ይመልከት፤ እኛ ውሃን ማንቧቧትን ያንቧቧን መሆናችንን፤ ከዚያ ምድርን በደካማ ቡቃያ መሰንጠቅን የሰነጠቅን፤ በውስጧም እህልን ወይንንም፤ እርጥብ ሳርንም፤ የዘይትም ወይራንም ዘንባባንም፤ ጭፍቆች አትክልቶችንም፤ ፍራፍሬንናም፤ ገለባን ያበቀልን መሆናችንን ይመልከት፡፡ ለእናንተም ለእንሰሶቻችሁም መጠቀሚያ ይሆን ዘንድ (ይህን ሰራን)፡፡

فَإِذَا جَآءَتِ ٱلصَّآخَّةُ ﴿٣٣﴾ يَوۡمَ يَفِرُّ ٱلۡمَرۡءُ مِنۡ أَخِيهِ ﴿٣٤﴾ وَأُمِّهِۦ وَأَبِيهِ ﴿٣٥﴾
وَصَٰحِبَتِهِۦ وَبَنِيهِ ﴿٣٦﴾ لِكُلِّ ٱمۡرِيٕٖ مِّنۡهُمۡ يَوۡمَئِذٖ شَأۡنٞ يُغۡنِيهِ ﴿٣٧﴾

**33-37.** አደንቋሪይቱ መከራ በመጣች ጊዜ፤ ሰው ከወንድሙ፤ ከእናቱም፤ ከአባቱም፤ ከሚስቱና ከልጁም፤ በሚሸሽበት ቀን ከእነርሱ ለየሰው ሁሉ በዚያ ቀን ከሌላው የሚያብቃቃው ሁኔታ አለው፡፡

وُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ مُّسْفِرَةٌ ﴿٣٨﴾ ضَاحِكَةٌ مُّسْتَبْشِرَةٌ ﴿٣٩﴾ وَوُجُوهٌ يَوْمَئِذٍ عَلَيْهَا غَبَرَةٌ ﴿٤٠﴾
تَرْهَقُهَا قَتَرَةٌ ﴿٤١﴾ أُوْلَٰٓئِكَ هُمُ ٱلْكَفَرَةُ ٱلْفَجَرَةُ ﴿٤٢﴾

**38-42.** ፊቶች በዚያ ቀን አብሪዎች ሳቂዎችና ተደሳቾችም ናቸው። ሌሎች ፊቶችም በዚያ ቀን በላያቸው ላይ ትብያ አለባቸው። ጥቁረት ትሸፍናቸዋለች፤ እነዚያ እነርሱ በአላህ ከሓዲያን እና በትዕዛዙ ላይ አመፀኞች ናቸው።

**ከማጨፍገግ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-42) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. ስለ ነብዩ (ﷺ) ትልቅነት፤
2. ነብዩ (ﷺ) በዚህ ወቀሳ ሳይቀየሙ ባለ ታሪኩን ይሰጡት ነበረው ክብር የሳቸውን ትልቅነት እንደሚያሳይ፤
3. ነብዩ (ﷺ) ወቀሳውን ሳይቀንሱና ሳያስተካክሉ ለህዝብ ጆሮ ማብቃታቸው ታማኝነታቸውን እንደሚሳይ፤
4. በእነዚህ አናቅፅ የአላህን ችሮታ፤ ጥልቅ ዕውቀት፤ አስደናቂ ጥበብና ትልቅነት መመልከት፤
5. ስራ ሰሪውን እንደሚያመለክት ሁሉ ፍጡሮችም ፈጣሪ እንዳላቸውና ሁሉን ቻይነቱን አዋቂነቱን አለ መረዳታቸው የሚገርም መሆኑን፤
6. የሰው ልጅ እድሜውን ሙሉ ቢሰግድና ቢፆም የአላህን ሀቅ በትክክል እንደማይወጣ፤ የቂያማ ቀን መከራ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ፤
7. የሰው ልጅ በዚህ አለም ሲኖር ያልተወቸው ግዴታዎች ከዚኛው አለም ምን ያህል ሊያስቸግሩት እንደሚችሉ፤
8. ለትንሳኤ አስደንጋጭነት የተነሳ ወዳጅ ከወዳጁ የሚርቅበት ሌላው ቀርቶ ወንድም ከወንድሙ ልጅ ከወላጆቹ ወዘተ የሚሸሽበት ቀን መሆኑን፤
9. የእምነት ውጤት በቂያማ ዕለት በፊት ላይ እንደሚያበራና አማኞች እንደሚደሰቱ ሁሉ የኩፍርም ውጤት እንደዚሁ በፊት ላይ ከሰል ሆኖ የካህዲያን ፊት በፍርሀት እንደሚጠቁር እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ ከማጨፍገግ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (81)
# የመጠቅለል ምዕራፍ
## (ሱረቱ አትተክዊር)

سُورَةُ التَّكْوِيرِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (29) ናቸው።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِذَا ٱلشَّمْسُ كُوِّرَتْ ﴿١﴾ وَإِذَا ٱلنُّجُومُ ٱنكَدَرَتْ ﴿٢﴾ وَإِذَا ٱلْجِبَالُ سُيِّرَتْ ﴿٣﴾ وَإِذَا ٱلْعِشَارُ
عُطِّلَتْ ﴿٤﴾ وَإِذَا ٱلْوُحُوشُ حُشِرَتْ ﴿٥﴾ وَإِذَا ٱلْبِحَارُ سُجِّرَتْ ﴿٦﴾ وَإِذَا ٱلنُّفُوسُ زُوِّجَتْ ﴿٧﴾
وَإِذَا ٱلْمَوْءُۥدَةُ سُئِلَتْ ﴿٨﴾ بِأَىِّ ذَنۢبٍ قُتِلَتْ ﴿٩﴾ وَإِذَا ٱلصُّحُفُ نُشِرَتْ ﴿١٠﴾ وَإِذَا ٱلسَّمَآءُ
كُشِطَتْ ﴿١١﴾ وَإِذَا ٱلْجَحِيمُ سُعِّرَتْ ﴿١٢﴾ وَإِذَا ٱلْجَنَّةُ أُزْلِفَتْ ﴿١٣﴾ عَلِمَتْ نَفْسٌ مَّآ أَحْضَرَتْ ﴿١٤﴾

**1-14.** ፀሐይ በተጠቀለለች ጊዜ፤✳[1] ከዋክብት በረገፉ ጊዜ፤ ተራራዎች በተናዱ ጊዜ፤ የአስር ወር እርጉዝ ግመሎች ያለጠባቂ በተተው ጊዜ፤ እንስሳት ሁሉ በተሰበሰቡ ጊዜ፤ ባህሮች በተቃጠሉ ጊዜ፤ ነፍሶች ከየአካሎቻቸው ጋር በተቆራኙ ጊዜ፤ ከነሕይወቷ የተቀበረችው ሴት ልጅ በምን ወንጀል እንደተገደለች፤ በተጠየቀች ጊዜ፤✳[2] ፁሑፎች በተዘረጉ ጊዜ፤ ሰማይ በተገሸለጠች ጊዜ፤ ገሀነምም በተነደደች ጊዜ፤ ገነት በተቀረበች ጊዜ፤ ነፍስ ሁሉ ከስራ ያቀረበችውን ታውቃለች፤

✳1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በትንሳኤ ቀን ፀሐይና ጨረቃ በአንድ ላይ ይጠቀለላሉ»

✳2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አል. ሙጊራህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በእርግጥ አላህ ለወላጆቹ ቅን አለመሆንን፤ ሴት ልጆችን በሕይወት መቅበርንና ልመናን በናንተ ላይ ክልክል አድርጓል። እንዲሁም አሉቧልታ፤ ጥያቄ ማዛትንና ገንዘብ ማባከንን ጠልቶላችኋል»

فَلَآ أُقْسِمُ بِٱلْخُنَّسِ ﴿١٥﴾ ٱلْجَوَارِ ٱلْكُنَّسِ ﴿١٦﴾ وَٱلَّيْلِ إِذَا عَسْعَسَ ﴿١٧﴾ وَٱلصُّبْحِ إِذَا تَنَفَّسَ ﴿١٨﴾
إِنَّهُۥ لَقَوْلُ رَسُولٍ كَرِيمٍ ﴿١٩﴾ ذِى قُوَّةٍ عِندَ ذِى ٱلْعَرْشِ مَكِينٍ ﴿٢٠﴾ مُّطَاعٍ ثَمَّ أَمِينٍ ﴿٢١﴾

**15-21.** (ሁኔታው ከሓዲያን እንደሚሉት አይደለም)። ተመላሾች በሆኑት (ከዋክብት) እምላለሁ። አንዳንድ ጊዜ ሂያጆች በሌላ ጊዜ ገቢዎች በሆኑት በሌሊቱም ጨለማውን በጠነሰሰ ጊዜ፤ በንጋትም በብርሃን በተነፈሰ ጊዜ እምላለሁ። እርሱ (ቁርኣን) የተከበረው መልዕክተኛ ጅብሪል ቃል ነው። የኃይል ባለቤት የሆነ፤ ከዙፋኑ ባለቤት ዘንድ ባለሟል የሆነ፤ በዚያ ስፍራ ትዕዛዙ ተሰሚ፤ የሆነ ታማኝ የሆነው መልዕክተኛ ቃል ነው።

وَمَا صَاحِبُكُم بِمَجْنُونٍ ﴿٢٢﴾ وَلَقَدْ رَءَاهُ بِٱلْأُفُقِ ٱلْمُبِينِ ﴿٢٣﴾
وَمَا هُوَ عَلَى ٱلْغَيْبِ بِضَنِينٍ ﴿٢٤﴾ وَمَا هُوَ بِقَوْلِ شَيْطَٰنٍ رَّجِيمٍ ﴿٢٥﴾

**22-25.** ነብያችሁ በፍፁም እብድ አይደለም። በግልፅ አድማስ ላይ ሆኖ ጅብሪልን በእርግጥ አይቶታል። እርሱም በሩቁ ወሬ ላይ ሰሳች (ንፉግ) አይደለም። እርሱም (ቁርኣን) የርጉም ሰይጣን ቃል አይደለም።

فَأَيْنَ تَذْهَبُونَ ﴿٢٦﴾ إِنْ هُوَ إِلَّا ذِكْرٌ لِّلْعَٰلَمِينَ ﴿٢٧﴾ لِمَن شَآءَ مِنكُمْ أَن يَسْتَقِيمَ ﴿٢٨﴾
وَمَا تَشَآءُونَ إِلَّآ أَن يَشَآءَ ٱللَّهُ رَبُّ ٱلْعَٰلَمِينَ ﴿٢٩﴾

**26-29.** ታዲያ ወዴት በሱ ጉዳይ ትሄዳላችሁ? እርሱ የዓለማት መገሰጫ* እንጂ ሌላ አይደለም። ከናንተ መካከል ቀጥተኛው ሰው መሆንን ለፈለገ ሁሉ መገሰጫ ነው። (ሰዎች ሆይ)፣ የዓለማት ጌታ የሆነው አላህ ካልሻ በስተቀር እናንተም አንድን ነገር አትሹም።

* (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ከነብያት መካከል አንድም ነብይ ተዓምራት ሳይሰጠውና በዚህም ሰዎች ደህንነትን ሳያገኙ ወይም በሱ ሳያምኑ የተላከ የለም። እኔ ደግሞ አላህ ወደኔ ያወረደውን መለኮታዊ ራዕይ ተሰጥቶኛል። በትንሳኤ ቀንም እኔ ከነሱ ይበልጥ ተከታይ ያለኝ እንድሆን እፈልጋለሁ»

(ለ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «የሙሐመድ ነፍስ በእጁ በሆነችው ጌታ እምላለሁ! ከአይሁድና ከክርስቲያኖች መካከል ስለኔ ሰምቶና በተላኩበት መልዕክት ሳያምን የሚሞት የለም ከእሳት ሰዎች ካልሆነ በስተቀር»

ከመጠቅለል ምዕራፍ (29) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- «ከእናንተ ቀጥተኛ መሆንን ለፈለገ ሰው» የሚለው የቁርኣን አንቀፅ ሲወርድ እነ አቡ ጀህል ይህማ እኛ እንደፈለግነው ነው ማለት ነው ብንፈልግ አስተካክለን ባንፈልግ ግን እንተዋለን በማለታቸው ነው ይህ የወረደው።

**ከመጠቅለል ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-29) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙቶ መነሳት ሒሳብ መኖሩ ቅንጣት ያህል የሚያጠራጥር እንደሆነ፤
2. ስለ ቂያማ መነሻና መድረሻ ሰፊ ማብራሪያ፤

3. ገነት የአማኞች ማረፊያ መሆንዋን በማውሳት ገሀነም ደግሞ የአጋሪዎች መኖሪያ መሆንዋን በመጥቀስ በእምነት ና በመልካም ስራ ላይ ግፊት ማሳደር፤
4. ከሽርክና ከወንጀል ማስፈራራትና ማስጠንቀቅ፤
5. በአላህ በስሞቹና በባህሪያቱ መማል እንደሚፈቀድ፤
6. ወህይና ነብይነት እውነት መሆኑን፤ ቁርኣን የአላህ ቃልመሆኑን፤ ነብዩ የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን፤
7. የመላዕኩ ጅብሪል ባህሪያትን ማስታወስ፤
8. ነብዩ (ﷺ) አጋሪዎች ከሚሏቸው ሁሉ የፀዱ መሆናቸውን መግለፅ፤
9. የሰው ልጆች ፍላጎት የአላህ ፍላጎት እንደሚቀድምና እሱ ያልሻው ነገር በዚህች አለም እንደማይከሰት እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የመጠቅለል ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (82)
## የመሰንጠቅ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ኢንፊጧር)

سُورَةُ الانفِطَارِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (19) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنفَطَرَتۡ ﴿١﴾ وَإِذَا ٱلۡكَوَاكِبُ ٱنتَثَرَتۡ ﴿٢﴾ وَإِذَا ٱلۡبِحَارُ فُجِّرَتۡ ﴿٣﴾
وَإِذَا ٱلۡقُبُورُ بُعۡثِرَتۡ ﴿٤﴾ عَلِمَتۡ نَفۡسٞ مَّا قَدَّمَتۡ وَأَخَّرَتۡ ﴿٥﴾

**1-5.** ሰማይ በተሰነጠቀች ጊዜ፤ ከዋክብትም ተበታትነው በወደቁ ጊዜ፤ ባህሮችም በተከፈቱና በተደባለቁ ጊዜ፤ መቃብሮችም በተገለባበጡና ሙታን በተነሱ ጊዜ፤ ማንኛይቱም ነፍስ የሰራችውንና ያልሰራችውን ታውቃለች።

يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ مَا غَرَّكَ بِرَبِّكَ ٱلۡكَرِيمِ ﴿٦﴾ ٱلَّذِي خَلَقَكَ فَسَوَّىٰكَ فَعَدَلَكَ ﴿٧﴾
فِيٓ أَيِّ صُورَةٖ مَّا شَآءَ رَكَّبَكَ ﴿٨﴾ كَلَّا بَلۡ تُكَذِّبُونَ بِٱلدِّينِ ﴿٩﴾

**6-9.** አንተ ሰው ሆይ፣ በቸሩ ጌታህ ምን አታለለህ? በዚያ በፈጠረህ፤ አካለ ሙሉም ባደረገህ፤ ባስተካከለህም፤ በፈለገው ቅርፅ በገጣጠመህ ጌታህ ምን አታለለህ። (ሰዎች ሆይ)፣ ተከልከሉ፤ በእውነት በፍርዱ ቀን ታስተባብላላችሁ።

ከመሰንጠቅ ምዕራፍ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በኡበይ ቢን ኸለፍ ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

وَإِنَّ عَلَيۡكُمۡ لَحَٰفِظِينَ ﴿١٠﴾ كِرَامٗا كَٰتِبِينَ ﴿١١﴾ يَعۡلَمُونَ مَا تَفۡعَلُونَ ﴿١٢﴾

**10-12.** በእናንተ ላይ ጠባቂዎች*[1] ያሉባችሁ ስትሆኑ፤ የተከበሩ ፀሐፊዎች የሆኑ*[2] (ተጠባባቂዎች)፤ የምትሰሩትን ሁሉ የሚያውቁ፤

*1 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) አቡ ሁረይራህ እንዳስተላፉት እንዲህ ብለዋል፡- «በቀንና በሌሊት ወደናንተ የሚመጡ መላዕክቶች አሉ። በአንድነት በፈጅርና በዐስር የሶላት ወቅቶች ይገናኛሉ። እነዚያ ለሊቱን ከናንተ ጋር የነበሩት ወደ አላህ ይወጣሉ። አላህም «ባሪያዎቼ በምን ሁኔታ ተዋቻኋቸው?»

እርሱ የእነርሱን መልስ ቀድሞ እያወቀ ሲል ይጠይቃቸዋል። እነርሱም «እየሰገዱ ሳለ ተውናቸው እየሰገዱ ሳሉም ወደነርሱ መጣን» በማለት ይመልሳሉ» ነብዩ (ﷺ) አክለውም«ከናንተ መካከል አንዱ በሶላቱ ላይ ከፋቲሓ በኋላ አሚን ካለ ሰማይ ላይ ያሉት መላዕክት እንዲሁ አሚን ይላሉ። እነዚህም ሁለት ቃሎች ሲገናኙ የሰውየው የቀድሞ ኃጢአቶች በሙሉ ይሰረዛሉ»

✳2 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ አባስ እንዳስተላፉት እንዲህ ብለዋል፡- «በናንተ ላይ ለተመረጡ መላዕክቶች መልካምና መጥፎ ስራዎች ሁሉ መፃፍ አለባቸው ሲል አዟቸዋል። ከዚያም እንዴት እንደሚፅፉትም አመላክቷቸው። አንድ ሰው አንድ መልካም ነገር ለመስራት ተነሳስቶ ባይሰራው አላህ መልካም ተግባርን ሙሉ ምንዳ ይፅፍለታል። እንዲሁም አንድን መልካም ነገር ለመስራት ተነሳስቶ በእርግጥ ቢሰራው ከአስር እስከ ሰባት መቶ የሚደርሱ ከዚያም በላይ ብዙ እጥፍ ይፃፍለታል። አንድ ሰው መጥፎ ተግባር ለመስራት ተነሳስቶ ባይፈፅመው አላህ የመልካምን ስራ ሙሉ ምንዳ ይፅፍለታል። እንዲሁም መጥፎ ተግባር ለመስራት ተነሳስቶ በእርግጥም ቢፈፅመው አላህ የአንድን መጥፎ ስራ ምንዳ ይፅፍለታል።»

إِنَّ ٱلۡأَبۡرَارَ لَفِي نَعِيمٖ ﴿١٣﴾ وَإِنَّ ٱلۡفُجَّارَ لَفِي جَحِيمٖ ﴿١٤﴾ يَصۡلَوۡنَهَا يَوۡمَ ٱلدِّينِ ﴿١٥﴾
وَمَا هُمۡ عَنۡهَا بِغَآئِبِينَ ﴿١٦﴾

**13-16.** እውነተኞቹ አማኞች በእርግጥም በገነት ውስጥ ናቸው። ከሓዲያንም በእርግጥ በገሀነም ውስጥ ናቸው። በፍርዱ ቀን ይገቧታል። እነርሱም ምን ጊዜም ከእርሷ ራቂዎች አይደሉም።

وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ﴿١٧﴾

**17.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የፍርዱ ቀን ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ?

ثُمَّ مَآ أَدۡرَىٰكَ مَا يَوۡمُ ٱلدِّينِ ﴿١٨﴾

**18.** ከዚያም የፍርዱ ቀን ምን እንደሆነ ምን አሳወቅህ?

يَوۡمَ لَا تَمۡلِكُ نَفۡسٞ لِّنَفۡسٖ شَيۡـٔٗاۖ وَٱلۡأَمۡرُ يَوۡمَئِذٖ لِّلَّهِ ﴿١٩﴾

**19.** (እርሱ) ማንኛይቱም ነፍስ ለሌላይቱ ነፍስ ምንም ማድረግ የማትችልበት ቀን ነው። ነገሩም ሁሉ በዚያ ቀን ለአላህ ብቻ ነው።

### ከመሰንጠቅ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-19) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-

1. ይህ ዓለም ለማንም ጠፊነቱን በየሰዓቱ የሚታዩ መለዋወጥ እንደሚያስረዳ፤
2. የሰው ልጅ የአላህን ፀጋ መካድና ማስተባበሉ ሙቶ መነሳትን መካዱን፤
3. የሰው ልጅ ለሁለተኛው ዓለም አማኝና ከሃዲ ተብሎ ለሁለት እንደሚከፈል፤
4. የቂያማ ቀን ጉዳይ የሰው ልጆች በደንብ እንደሚዘጋጁበት ማስታወስ፤

5. የዚያ ዕለት ስልጣኑ የአላህ ብቻ መሆኑን፤
6. የመጨረሻው ዓለም አላህ ይጠብቀንና ብዙ አስደንጋጭ ክስተቶች እንደሚከሰቱ፤
7. የአላህ ፀጋዎች ብዙ መሆናቸውን በማስታወስ ልናመሰግነው እንደሚገባ፤
8. የትንሳኤ ቀን ያስተባበሉ ከሓዲያንን ማውገዙ፤
9. የሰው ልጅ እያንዳንዳችን ተግባሮቻችን የሚመዘግቡ መላኢኮች አብረውን እንዳሉ፤
10. ትክክለኛ አማኞች በጀነት ሲጣቀሙ አመፀኛ ከሓዲያን ግን በጀሀነም እንደሚቀጡ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የመሰንጠቅ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (83)
## የሰላቢዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልሙጦፊፊን)

سُورَةُ المُطَفِّفِينَ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (36) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَيۡلٞ لِّلۡمُطَفِّفِينَ ١ ٱلَّذِينَ إِذَا ٱكۡتَالُواْ عَلَى ٱلنَّاسِ يَسۡتَوۡفُونَ ٢
وَإِذَا كَالُوهُمۡ أَو وَّزَنُوهُمۡ يُخۡسِرُونَ ٣ أَلَا يَظُنُّ أُوْلَٰٓئِكَ أَنَّهُم مَّبۡعُوثُونَ ٤
لِيَوۡمٍ عَظِيمٖ ٥ يَوۡمَ يَقُومُ ٱلنَّاسُ لِرَبِّ ٱلۡعَٰلَمِينَ ٦

**1-6.** ሰላቢዎች ሲሸጡ (አንጠፍጣፊዎች) ሁሉ ወዮላቸው፤ ለእነዚያ ከሰዎች ለመግዛት ባስሰፈሩ ጊዜ የሚያስሞሉ፤ እነርሱም (ለሰዎች) በሰፈሩ ወይም በመዘኑላቸው ጊዜ የሚያጎሉ (ለሆኑት)። እነዚያ እነርሱ ተቀስቃሾች መሆናቸውን በትክክል አያውቁምን? በታላቁ ቀን፤ ሰዎች ሁሉ ለዓለማት ጌታ (ፍርድ) በሚቆሙበት ቀን (ተቀስቃሾች መሆናቸውን)።

ከሰላቢዎች (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ወደ መዲና በተሰደዱ ጊዜ የመዲና ሰዎች በስፍርና በሚዛን ማጭበርበር የታወቁ ነበሩና እነሱን ለማረም ነው ይህ የወረደው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ) (ከዛም በኋላ በጣም አስተካካዮች ሆኑ)

كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلۡفُجَّارِ لَفِي سِجِّينٖ ٧ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا سِجِّينٞ ٨ كِتَٰبٞ مَّرۡقُومٞ ٩ وَيۡلٞ
يَوۡمَئِذٖ لِّلۡمُكَذِّبِينَ ١٠ ٱلَّذِينَ يُكَذِّبُونَ بِيَوۡمِ ٱلدِّينِ ١١ وَمَا يُكَذِّبُ بِهِۦٓ إِلَّا كُلُّ مُعۡتَدٍ
أَثِيمٍ ١٢ إِذَا تُتۡلَىٰ عَلَيۡهِ ءَايَٰتُنَا قَالَ أَسَٰطِيرُ ٱلۡأَوَّلِينَ ١٣ كَلَّاۖ بَلۡۜ رَانَ عَلَىٰ قُلُوبِهِم مَّا كَانُواْ
يَكۡسِبُونَ ١٤ كَلَّآ إِنَّهُمۡ عَن رَّبِّهِمۡ يَوۡمَئِذٖ لَّمَحۡجُوبُونَ ١٥ ثُمَّ إِنَّهُمۡ لَصَالُواْ ٱلۡجَحِيمِ ١٦
ثُمَّ يُقَالُ هَٰذَا ٱلَّذِي كُنتُم بِهِۦ تُكَذِّبُونَ ١٧

**7-17.** በእውነት የካሓዲያን መጽሐፍ በእርግጥ በሲጂን ውስጥ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሲጂን ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ?

የታተመ መጽሐፍ ነው። ለአስተባባዮች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮውላቸው። ለእነዚያ በፍርድ ቀን ለሚያስተባብሉት። በእርሱም ወሰን አላፊ ኃጢአተኛ ሁሉ እንጂ ሌላ አያስተባብልም። አንቀፆቻችን በእርሱ ላይ በተነበቡ ጊዜ እኒህ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ተረቶች ናቸው ይላል። ይከልከሉ፤ ይልቁንም በልቦቻቸው ላይ ይሰሩት የነበሩት ኃጢአት ደገደገባቸው። ይከልከሉ። እነርሱ በዚያ ቀን ጌታቸውን ከማየት ተጋራጆች ናቸው። ከዚያ እነርሱ በእርግጥ ገሀነም ገቢዎች ናቸው። ከዚያ ይህ ያ በእርሱ ታስተባብሉበት የነበራችሁት ነው ይባላሉ።

كَلَّآ إِنَّ كِتَٰبَ ٱلْأَبْرَارِ لَفِى عِلِّيِّينَ ﴿١٨﴾ وَمَآ أَدْرَىٰكَ مَا عِلِّيُّونَ ﴿١٩﴾ كِتَٰبٌ مَّرْقُومٌ ﴿٢٠﴾
يَشْهَدُهُ ٱلْمُقَرَّبُونَ ﴿٢١﴾ إِنَّ ٱلْأَبْرَارَ لَفِى نَعِيمٍ ﴿٢٢﴾ عَلَى ٱلْأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ﴿٢٣﴾ تَعْرِفُ فِى
وُجُوهِهِمْ نَضْرَةَ ٱلنَّعِيمِ ﴿٢٤﴾ يُسْقَوْنَ مِن رَّحِيقٍ مَّخْتُومٍ ﴿٢٥﴾ خِتَٰمُهُۥ مِسْكٌ ۚ وَفِى ذَٰلِكَ
فَلْيَتَنَافَسِ ٱلْمُتَنَٰفِسُونَ ﴿٢٦﴾ وَمِزَاجُهُۥ مِن تَسْنِيمٍ ﴿٢٧﴾ عَيْنًا يَشْرَبُ بِهَا ٱلْمُقَرَّبُونَ ﴿٢٨﴾

**18-28.** በእውነቱ የእውነተኞቹ ምዕመናን መጽሐፍ በዒሊዩን ውስጥ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ዒሊዩንም ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ? የታተመ መጽሐፍ ነው። የአላህ ባለሟሎች (ይጣዱታል) ይጠብቁታል። እውነተኞችም ምዕመናን በእርግጥም በድሎት ገነት ውስጥ ናቸው። በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ የተደገፉ ሆነው ይመለከታሉ። በፊቶቻቸው ላይ የድሎትን ውበት ታያለህ። ተጣርቶ ከታተመ ወይን ጠጅ ይጠጣሉ። ማተሚያው ሚስክ ከሆነ። በዚህም ተሽቀዳዳሚዎች ይሽቀዳደሙ። መበረዣውም (ማብቂያዋም) ከተስኒም ነው። የአላህ ባለሟሎቹ ከእርሷ የሚጠጡላት ምንጭ ናት።

إِنَّ ٱلَّذِينَ أَجْرَمُوا۟ كَانُوا۟ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ يَضْحَكُونَ ﴿٢٩﴾ وَإِذَا مَرُّوا۟ بِهِمْ يَتَغَامَزُونَ ﴿٣٠﴾
وَإِذَا ٱنقَلَبُوٓا۟ إِلَىٰٓ أَهْلِهِمُ ٱنقَلَبُوا۟ فَكِهِينَ ﴿٣١﴾ وَإِذَا رَأَوْهُمْ قَالُوٓا۟ إِنَّ هَٰٓؤُلَآءِ لَضَآلُّونَ ﴿٣٢﴾
وَمَآ أُرْسِلُوا۟ عَلَيْهِمْ حَٰفِظِينَ ﴿٣٣﴾ فَٱلْيَوْمَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُوا۟ مِنَ ٱلْكُفَّارِ يَضْحَكُونَ ﴿٣٤﴾
عَلَى ٱلْأَرَآئِكِ يَنظُرُونَ ﴿٣٥﴾

**29-35.** እነዚያ በአላህ ላይ ያመፁት በእነዚያ በአላህ ባመኑት በእርግጥ ይስቁ ነበር። በእነርሱም አጠገብ ላይ ባለፉ ጊዜ ይጠቃቀሙባቸው (ይጠቃቀሱባቸው) ነበር። ወደ ቤተሰቦቻቸውም በተመለሱ ጊዜ በመሳለቃቸው ተደሳቾች ሆነው

ይመለሱ ነበር። ባዩዋቸውም ጊዜ፡- እነዚህ በእርግጥ ተሳሳቾች ናቸው ይሉ ነበር። በእነርሱ ላይ ተጠባባቂዎች ተደርገው ያልተላኩ ሲሆኑ። ዛሬ (በትንሳኤ ቀን) ግን እነዚያ በትክክል በአላህ ያመኑት ሰዎች በባለ አጎበር አልጋዎች ላይ ሆነው የሚመለከቱ ሲሆኑ በከሓዲያን* ላይ ይስቃሉ።

* የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ ኢብኑ ማሊክ እንዳስተላፉት አንድ ሰው የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላህ ከሓዲያንን በትንሳኤ ቀን በፊታቸው እንደተደፉ ይሰበስባቸዋልን? ሲል የአላህ መልዕክተኛን ጠየቀ። እሳቸውም «ቀድሞውኑ በሁለት እግሮቹ እንዲሄድ ያደረገው እሱ ሆኖ ሳለ በፊቱ ተደፍቶ እንዲሄድ ማድረግ አይችልምን?» ብለው አሉ። ቀታዳህም «በእሱ ክብር ይሁንብኝ እንዴታ!» አለ።

هَلۡ ثُوِّبَ ٱلۡكُفَّارُ مَا كَانُواْ يَفۡعَلُونَ ٣٦

36. ከሓዲያን ይሰሩት የነበሩትን (ዋጋ) ተመነዱን? (ይላሉ)።

**ከሰላቢዎች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-36) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በሚዛንም ሆነ በስፍር ማታለል ክልክል መሆኑን፤
2. የአብራሮች መዝገብ ምንዳቸው ምን እንደሚመስል፤
3. ከሞት በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ መነሳት የማይቀር ሃቅና ትክክለኛ መሆኑን፤
4. ያመፀኞች መዝገብ ከሰባት ምድር በታች እንደሆነ፤
5. በአላህ በተዓምሮቹና በሙቶ መነሳት የሚያስተባብሉ ሁሉ ከፍተኛ ቅሬታ እንደሚጠብቃቸው፤
6. በወንጀል ላይ ከመዘውተር ማስጠንቀቅና ንሰሀ አለማግባት (ተውበት አለማድረግ) ቀልብን እንደሚያጠቁር አበክሮ መምከር፤
7. ፈሪሀያንን ማሞገስና በጀነት ያዘጋጀላቸውን በምሳሌ አድርጎ መግለፅ፤
8. የጀነትን ፀጋ ለማግኘት መልካም ስራን ማብዛት እንደሚያስፈልግ በይፋ ማሳመን፤
9. በአላህ ላይ ማመፅን ማውገዝና ማንቋሸሽ፤
10. የኢስላም ዳዕዋ ሲጀመር በመካ ሙስሊሞች ላይ ስለደረሰባቸው ስቃይና መከራ መገለጫ በጥቂቱ፤
11. ሙዕሚኖች በጀነት ሆነው ሙሽሪኮችን በገሀነም ውስጥ ሲሰቃዩ እንደሚያይዋቸው፤
12. አላህ ወዳጆቹን የሚያስከብርና ጠላቶቹን የሚያዋርድ ጌታ ነው። እውነተኞች አማኞች በአኼራ አላህን የሚያዩት ሲሆኑ ከሓዲያን ግን ጌታቸውን ለማየት እንደማይችሉ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የመሰንጠቅ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (84)
## የመቀደዱ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልኢንሺቃቅ)

## سُورَةُ الانشِقَاقِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (25) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِذَا ٱلسَّمَآءُ ٱنشَقَّتۡ ١ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٢ وَإِذَا ٱلۡأَرۡضُ مُدَّتۡ ٣
وَأَلۡقَتۡ مَا فِيهَا وَتَخَلَّتۡ ٤ وَأَذِنَتۡ لِرَبِّهَا وَحُقَّتۡ ٥ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡإِنسَٰنُ إِنَّكَ كَادِحٌ إِلَىٰ
رَبِّكَ كَدۡحٗا فَمُلَٰقِيهِ ٦

**1-6.** ሰማይ በተቀደደች (በተሰነጠቀች) ጊዜ፤ የጌታዋንም ትዕዛዝ በሰማች ጊዜ፤ ልትሰማ ተገባትም፤ ምድርም በተለጠጠች ጊዜ፤ በውስጧ ያለውንም ሙታንን ሁሉ በጣለችና ባዶ በሆነች ጊዜ፤ ለጌታዋም በሰማች ጊዜ መስማት ተገባትም፤ (ሰው ሁሉ የስራውን ውጤት ያገኛል)፤ አንተ ሰው ሆይ፣ አንተ ጌታህን በሞት እስከምትገናኝ ድረስ ልፋትን ለፊ ነህ። ተገናኚውም ነህ።

فَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ بِيَمِينِهِۦ ٧ فَسَوۡفَ يُحَاسَبُ حِسَابٗا يَسِيرٗا ٨ وَيَنقَلِبُ إِلَىٰٓ
أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورٗا ٩ وَأَمَّا مَنۡ أُوتِيَ كِتَٰبَهُۥ وَرَآءَ ظَهۡرِهِۦ ١٠ فَسَوۡفَ يَدۡعُواْ ثُبُورٗا ١١
وَيَصۡلَىٰ سَعِيرًا ١٢ إِنَّهُۥ كَانَ فِيٓ أَهۡلِهِۦ مَسۡرُورًا ١٣ إِنَّهُۥ ظَنَّ أَن لَّن يَحُورَ ١٤ بَلَىٰٓۚ إِنَّ رَبَّهُۥ
كَانَ بِهِۦ بَصِيرٗا ١٥

**7-15.** ያ፣ መጽሐፉን በቀኝ እጅ የተሰጠ ሰው በእርግጥ ቀላልን ምርመራ ይመረምመራል። ወደ ቤተሰቦቹም ተደሳች ሆኖ (በደስታ) ይመለሳል። ያ፣ መጽሐፉን በጀርባው በኩል የተሰጠ ሰው ግን ዋ፣ ጥፋቴ በማለት ጥፋትን በእርግጥ ይጠራል። የተጋጋመች እሳትንም ይገባል። እርሱ በቤተሰቡ ውስጥ ተደሳችና፤ እርሱም ወደ አላህ እንደማይመለስ ያስብ ነበርና ነው። አይደለም ይመለሳል፤ ጌታው በርሱ መመለስ አዋቂ ነው።

فَلَآ أُقۡسِمُ بِٱلشَّفَقِ ﴿١٦﴾ وَٱلَّيۡلِ وَمَا وَسَقَ ﴿١٧﴾ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا ٱتَّسَقَ ﴿١٨﴾ لَتَرۡكَبُنَّ طَبَقًا عَن طَبَقٖ ﴿١٩﴾

**16-19.** (ጉዳዩ እንዳላችሁት አይደለም)። በወጋገኑ፤ እምላለሁ። በሌሊቱና በሰበሰበውም ሁሉ፤ በጨረቃም በሞላ ጊዜ (እምላለሁ)። ከአንድ ደረጃ በኋላ ወደ ሌላ ደረጃ ትለዋወጣላችሁ፤ (ከአንድ እርከን ወደ ሌላ ትሸጋገራላችሁ።)

فَمَا لَهُمۡ لَا يُؤۡمِنُونَ ﴿٢٠﴾ وَإِذَا قُرِئَ عَلَيۡهِمُ ٱلۡقُرۡءَانُ لَا يَسۡجُدُونَ۩ ﴿٢١﴾ بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ يُكَذِّبُونَ ﴿٢٢﴾ وَٱللَّهُ أَعۡلَمُ بِمَا يُوعُونَ ﴿٢٣﴾ فَبَشِّرۡهُم بِعَذَابٍ أَلِيمٍ ﴿٢٤﴾ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمۡ أَجۡرٌ غَيۡرُ مَمۡنُونِۭ ﴿٢٥﴾

**20-25.** የማያምኑት ለእነርሱ ምን አላቸው? (ለምን አያምኑም?) በእነርሱ ላይ ቁርአን በተነበበ ጊዜ የማይሰግዱት ለእነርሱም ምን አላቸው? (ለምን አይሰግዱም?) በእርግጥ እነዚያ የካዱት በትንሳኤ ቀን ያስተባብላሉ። አላህ በልቦቻቸው የሚቋጥሩትን ሁሉ አዋቂ ነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በአሳማሚ ቅጣትም አብስራቸው። ግን እነዚያ በአላህ ያመኑትና መልካሞችን የሰሩ ሁሉ ለእነርሱ የማያቋርጥ ምንዳ አላቸው።*

* የተሟለ ዕረፍት በጀነት ብቻ ነው። ከዚያ በፊት ያሉት ዕረፍቶች ሁሉ ጊዜያዊ እረፍቶች ናቸው። የተሟሉም አይደሉም። አህመድ ኢብኑ ሐንበል«ረፍት መቼ ነው ተብለው ሲጠየቁ እግርህ የጀነት ምድር ስትረግጥ ብቻ እረፍ»በማለት መልስ ሰጥተዋል። መስሩቅ የተባሉ አሊም ሱጅድ እንዳደረጉ ይተኙ ነበርና ምነው እረፍት ቢያደርጉ ተብለው ቢጠየቁ እኔም እኮ እረፍቴ ነው የፈለኩት ማለታቸው ተዘግቧል።

**ከመቀደዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-25) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የሙቶ መነሳትን ነገር ሀቅነት ማረጋገጥ፤
2. በአላህ የሚያምንና በአግባቡ የሚፈሩ ሁሉ ገር ምርመራ እንደሚመረመሩ፤
3. የሰው ልጅ ከጌታው ጋር መገናኘቱ አይቀሬ መሆኑን በግልፅ ማስረዳት፤
4. በሱ ያላመነና መልካም ስራ የሌለው ምርመራው ከባድ እንደሚሆንበት፤
5. በዱንያ መደሰትና በስሜት መሳብ ያለማመን ምክንያት መሆኑን፤
6. የሰው ልጅ ከአንዱ ሁኔታ ወደ ሌላ ሁኔታ እየተዘዋወረ ጀነት ወይም ጀሀነም እስከሚደርስ እንደሚጓዝ፤
7. በአላህ አለማመን በጣም የሚገርም መጥፎ ተግባር መሆኑን፤
8. አላህ የሰው ልጅ የተነገረውንና የሰራውን ብቻ ሳይሆን በልቡ ያሰበውንም የሚያውቅ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የመቀደድ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (85)
## የቡሩጆች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ቡሩጅ)

سُورَةُ البُرُوجِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (22) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلۡبُرُوجِ ١ وَٱلۡيَوۡمِ ٱلۡمَوۡعُودِ ٢ وَشَاهِدٖ وَمَشۡهُودٖ ٣

**1-3.** የቡሩጆች ባለቤት በሆነችው ሰማይ፣ በዚያ በተቀጠረውም ቀን፣ በመስካሪና በሚመሰከርበትም እምላለሁ።

قُتِلَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡأُخۡدُودِ ٤ ٱلنَّارِ ذَاتِ ٱلۡوَقُودِ ٥ إِذۡ هُمۡ عَلَيۡهَا قُعُودٞ ٦
وَهُمۡ عَلَىٰ مَا يَفۡعَلُونَ بِٱلۡمُؤۡمِنِينَ شُهُودٞ ٧

**4-7.** የጉድቡ* ባለቤቶች ተረገሙ። የማገዶ ባለቤት በሆነችው እሳት ባለቤቶች። ከእነርሱ በምዕመኖች ላይ የሚሰሩትን ለመመልከት በርሷ (አፋፍ) ላይ ተቀማጮች በሆኑ ጊዜ (ተረገሙ)።

*✷ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡«ከእናንተ በፊት ይኖሩ በነበሩት ሕዝቦች መካከል አንድ ንጉስ ነበር። ይህ ንጉስ አንድ አስማተኛም ነበረው። አስማተኛው ሲያረጅ ለንጉሱ «እኔ እያረጀሁ ነኝና አንድ አስማት የማስተምረውን ልጅ ስጠኝ» አለው። ንጉሱም የአስማተኛውን ቃል ሰምቶ አስማት የሚያስተምረውን ልጅ ለአስማተኛው ላከለት። ልጁ ዘወትር ወደ አስማተኛው ሰውዬ በሚጓዝበት ወቅት መንገድ ላይ አንድ ባህታዊ ሰው የሚናገረውን ቁጭ ብሎ በማድመጥ ባህታዊው በሚናገረው ንግግር ይደነቅ ነበር። ሁልጊዜ ወደ አስማተኛው ሲያመራ ባህታዊውን አዳምጦ ወደ አስማተኛው ሲሄድ አስማተኛው ይደበድበዋል። ስለዚህ ይህን ጉዳይ ለባህታዊው አጫወተው። ባህታዊውም «በማንኛውም ወቅት ወደ አስማተኛው ስትሄድ «ለአስማተኛው ቤተሰቦቼ በስራ ወጥረውኝ ነው» በላቸው» አለው። ልጁም ይህን በመፈፀም ለትንሽ ጊዜ ቆየ። ከዕለታ አንድ ቀን ወደ ባህታዊው እየመጣ ሳለ አንድ ትልቅ እንስሳ መንገዱን ላይ ተጋድሞ ሰዎችን ማለፊያ አሳጥቷቸው ነበር። ይህን ጊዜ «ዛሬ ከአስማተኛው እና ከባህታዊው ማን የተሻለ እንደሆነ አውቃለሁ» አለና ትንሽ ድንጋይ አንስቶ «አላህ ሆይ! የባህታዊው ድርጊትና ባህሪይ ከአስማተኛው ይበልጥ ባንተ ዘንድ ተወዳጅ ከሆነ ሰዎች መንገዱን እንዲያቋርጡ ይህን እንስሳ ግደለው» ብሎ እንሰሳውን በድንጋይ ሲመታው ሞተ። ሰዎቹም መንገዱን አቋረጡ። ልጁም ወደ ባህታዊው መጣና ስለ ሁኔታው አጫወተው። ባታዊውም «ልጄ ሆይ! ዛሬ አንተ ከኔ የተሻልክ*

ነህ! እኔ የምመለከተውን ትልቅ ነገር ይዘሃል። ወደ እስር ቤትም ትወረወራለህ በእስር ላይ ሳለህም ለአሳሪዎችህ ስለኔ ምንም ነገር አትንገራቸው» አለው። ልጁም በተፈጥሮ በዓይነ. ስውርነት፤ በቁምጥና፤ በለምጥና በሌሎች በሽታዎች የተጠቁትን ሰዎች ማከም ጀመረ። በዚህን ጊዜ ዓይነ. ስውር የነበረ የንጉሱ አማካሪ ስለዚህ ልጅ ዝና ሰምቶ ብዙ ስጦታዎችን ይዞ ወደ ልጅ በመምጣት «አንተ ካዳንከኝ እነዚህ ሁሉ ስጦታዎች ያንተ ናቸው» አለው። ልጁም «እኔ ማንንም አላድንም። ሰዎችን ሁሉ የሚያድነው አላህ ብቻ ነው። በአላህ ካመንክ አላህን ብቻ ካመለክ አላህ ያድንሃል» አለው። ሰውየውም እንደተባለው በአላህ አመነ። አላህም ከበሽታው አዳነው። ከዚያም ሰውየው ወደ ንጉሱ በመምጣት ቀድሞ ይቀመጥበት በነበረው ቦታ ለይ ተቀመጠ። ንጉሱም «የዓይኖችህን ብርሃኖች ማን መለሰልህ?» ሲል ጠየቀው። ሰውየውም «ጌታ አላህ ነው!» ሲል መለሰለት። ንጉሱም ሰውየውን ከስልጣን አውርዶ ስለ ልጁ እስኪነግረው ድረስ ያሰቃየው ነበር። ልጁም ተይዞ ንጉሱ ፊት ቀረበ። ንጉሱም «ልጄ ሆይ! የአስማት ትምህርትህን ዓይነ. ስውራን፤ ቆማጣዎችንና ለምጣሞችን የማዳን ደረጃ ላይ ደረስን?» ሲል ጠየቀው። ልጁም «እኔ ማንንም አላድንም። አላህ ብቻ ነው ማከም የሚችለው» አለው። ንጉሱም ልጁ ባህታዊውን እስሚጠቁመው ድረስ ያሰቃው ነበር። ባህታዊውም ተይዞ ንጉሱ ፊት ቀረበ። «ይህን ሃይማኖትህን ትተህ ወደ ጣኦት አምላኪነት ተመለስ» ሲባል ባህታዊው አሻፈረኝ አለ። ንጉሱም መጋዝ እንዲመጣለት ካዘዘ በኋላ በባህታዊው መህል አናት ላይ በማስቀመጥ ባህታዊውን ሁለት ቦታ ላይ ሰነጠቀው። ቀጠለና አማካሪውን አስመጥቶ «ይህን ሃይማኖትህን ትተህ ወደ ጣኦት አምልኮት ተመለሰስ» አለው። አማካሪው ግን አሻፈረኝ በማለቱ እሱንም እንደ ባህታዊው ከመህል አናቱ በመጀመር ለሁለት ተከፍሎ እስኪወድቅ ድረስ በመጋዝ ቆረጠው። ከዚያም ልጁን አስቀርቦ ይህን ሃይማኖትህን ትተህ ወደ ጣኦት አምልኮት ተመለስ» ሲለው ልጁ አሻፈረኝ በማለቱ ንጉሱ አሽከሮቹን «እንዲህ እንዲህ የሚባል ተራራ ጫፍ ላይ ውሰዱትና ወደ ጣኦት አምልኮት ከተመለሰ መልካም ያለበለዚያ ግን ከተራራው ጫፍ ላይ ወርወሩት። ሲል አዘዛቸው። አሽከሮቹም የንጉሱን ትዕዛዝተ ተቀብለው ለመፈፀም ልጁን ይዘውት ወደ ተራራው ወጡ። በዚህም ጊዜ ልጁ «አላህ ሆይ! በምትፈለግው ነገር ከነርሱ ጠብቀኝ» አለ። ልጁ ይህን በማለቱ ተራራው ተንቀጠቀጠና አሽከሮቹ ከተራራው ላይ ሲወድቁ ልጁ ግን ወደ ንጉሱ መጣ። ንጉሱም «አጃቢዎችህ ምን ሰሩ?» ሲል ጠየቀው። ልጁም «አላህ ከነሱ ጠበቀኝ» በማለት መለሰለት። ንጉሱም አሁንም ሌሎች አሽከሮቹን «በመርከብ ወደ መህል ባህር ውሰዱትና ወደ ጣኦት አምልኮቱ ከተመለሰ ደህና ያለዚያ ግን ወደ ባህሩ ወርውሩት» ሲል አዘዛቸው። እነሱም ልጁን ወደ ባህሩ ይዘውት ሲሄዱ ልጁ «አላህ ሆይ! በምትፈልገው ነገር ከነሱ ጠብቀኝ» አለ። ይህን ጊዜ መርከቧ በማዕበል ተመታ ሁሉም አጅበውት የነበሩት ሰዎች ባህሩ ውስጥ ወደቁ ልጁ ግን አሁንም ወደ ንጉሱ መጣ። ንጉሱ አሁንም አጃቢዎችህ ምን ሰሩ?» በማለት ጠየቀው። እሱም «አላህ ከነሱ ጠበቀኝ» ሲል መለሰለት። ንግግሩን ቀጠል አድርጎ «እኔ የማዝህን እስካልፈፀምክ ድረስ ፈፅሞ ልትገድለኝ አትችልም» አለው። «ያ ትዕዛዝህ ምንድ ነው?» አለው። ልጁም «ከፍታ ባለው ስፍራ ሰዎችን ሁሉ ሰብስብ። እናም ከግንድ ጋር እሰረኝ። ከቀስት መያዣ ኮሮጆዬ ቀስት በመውሰድ «በአላህ ስም የዚህ ልጅ ጌታ!» ብለህ ግደለኝ። ይህን ከፈፀምክ ትገድለኛለህም» አለው። ንጉሱም እንደተባለው ከፍ ያለ ቦታ ላይ ሰዎችን ከሰበሰበ በኋላ ልጁን ከግንድ ጋር አሰረው። ከዚያም ከልጁ የቀስት ኮሮጆ ቀስት በመውሰድ ከደጋኑ ጋር አያያዘው። በመቀጠልም «በአላህ ስም በዚህ ልጅ ጌታ» በማለት ቀስቱን ወደ ልጁ ወረወረው። ቀስቷም የልጁን ግንባር ላይ ተሰካችና ሞተ። ሰዎቹም «እኛ በልጁ ጌታ አምነናል! እኛ በልጁ ጌታ አምነናል! እኛ በልጁ ጌታ አምነናል! በማለት ማመናቸውን በአደባባይ አወጁ። ንጉሱም ጥልቅ ጉድግዶች በየመንገዱ እንዲቆፈሩ አዘዘ። ጉድጓዶቹም ተቆፈሩ። በጉድጓዶቹም ውስጥ እሳት እንዲቀጣጠል አዘዘ። ንጉሱ እሳቱ እንዲቀጣጠል ያዘዘበት ዋና ምክንያት ወደ ጣኦት አምልኮት የማይመለስ ሰው ሁሉ በእሳት ውስጥ እንዲቃጠል በመፈለጉ ነው። ይህም በተግባር ተፈፀመ። አንዲት ሕፃን የያዘች እናትም ወደ ጉድጓዱ መጣች። ዳሩ ግን ለህፃኑ ስትል ቀስ በቀስ ከጉድጓዱ ስታፈገፍግ ህፃኑ እንዲህ ሲል ተናገረ፤ እናቴ ሆይ! ታጋሽ ሁኚ። አንቺ በእውነት ላይ ነው ያለሽው። እሷም ሕፃኑ እንዲህ ሲላት አብራው በጉድጓድ ውስጥ ወደ ሚቀጣጠለው እሳት ገባች»

وَمَا نَقَمُواْ مِنْهُمْ إِلَّآ أَن يُؤْمِنُواْ بِٱللَّهِ ٱلْعَزِيزِ ٱلْحَمِيدِ ﴿٨﴾ ٱلَّذِى لَهُۥ مُلْكُ ٱلسَّمَٰوَٰتِ وَٱلْأَرْضِ ۚ وَٱللَّهُ عَلَىٰ كُلِّ شَىْءٍ شَهِيدٌ ﴿٩﴾

**8-9.** ከእነርሱም በአላህ በአሸናፊውና በምስጉኑ ጌታ ማመናቸውን እንጂ ሌላን ምንንም አልጠሉም። በዚያ የሰማይና የምድር ንግስና ለእርሱ ብቻ በሆነው (አላህ ማመናቸውን)። አላህ በነገሩ ሁሉ ላይ መስካሪ ነው አዋቂ ነው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ فَتَنُواْ ٱلْمُؤْمِنِينَ وَٱلْمُؤْمِنَٰتِ ثُمَّ لَمْ يَتُوبُواْ فَلَهُمْ عَذَابُ جَهَنَّمَ وَلَهُمْ عَذَابُ ٱلْحَرِيقِ ﴿١٠﴾

**10.** እነዚያ ምዕመናንና ምዕመናትን ያሰቃዩና ከዚያ ያልተፀፀቱ ሁሉ ለእነርሱ የገሀነም ቅጣት አለላቸው። ለእነርሱም የመቃጠሉ ስቃይ አልላቸው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ لَهُمْ جَنَّٰتٌ تَجْرِى مِن تَحْتِهَا ٱلْأَنْهَٰرُ ۚ ذَٰلِكَ ٱلْفَوْزُ ٱلْكَبِيرُ ﴿١١﴾

**11.** እነዚያ በአላህ ያመኑትን መልካም ስራዎችን የሰሩ ሁሉ ለእነርሱ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች አሏቸው። ይህ ታላቅ መታደል ነው።

إِنَّ بَطْشَ رَبِّكَ لَشَدِيدٌ ﴿١٢﴾

**12.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የጌታህ ኃይል መያዝ ብርቱ ነው።

إِنَّهُۥ هُوَ يُبْدِئُ وَيُعِيدُ ﴿١٣﴾ وَهُوَ ٱلْغَفُورُ ٱلْوَدُودُ ﴿١٤﴾ ذُو ٱلْعَرْشِ ٱلْمَجِيدُ ﴿١٥﴾ فَعَّالٌ لِّمَا يُرِيدُ ﴿١٦﴾

**13-16.** እነሆ እርሱ መፍጠርን ይጀምራል፤ ይመልሳልም። እርሱም ምህረቱ ብዙ ወዳድ ነው። የዙፋኑ ባለቤት የላቀው ነው። የሚሻውን ሁሉ ሰሪ (ፈፃሚ) ነው።

هَلْ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلْجُنُودِ ﴿١٧﴾ فِرْعَوْنَ وَثَمُودَ ﴿١٨﴾

**17-18.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የእነዚያ ነብያትን ያስተባበሉ ሰራዊቶች የፊርዓውንና የሰሙድ ወሬ ደርሶሃልን?

بَلِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ فِي تَكۡذِيبٖ ﴿١٩﴾ وَٱللَّهُ مِن وَرَآئِهِم مُّحِيطُۢ ﴿٢٠﴾

**19-20.** በእውነት እነዚያ በአላህ የካዱት ሰዎች ሁሉ እውነትን በማስተባበል ውስጥ ናቸው። አላህም በዙሪያቸው በዕውቀቱ ከባቢ ነው።

بَلۡ هُوَ قُرۡءَانٞ مَّجِيدٞ ﴿٢١﴾ فِي لَوۡحٖ مَّحۡفُوظِۭ ﴿٢٢﴾

**21-22.** ይልቁንም እርሱ የተከበረ ቁርኣን ነው። የተጠበቀ በሆነ ሰሌዳ ውስጥ ነው።

**ከቡሩጆች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-22) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ትክክለኛ አማኝ ለእምነቱ ሲል በሁሉ ነገር መስዋዕት እንደሚከፍል፤
2. ከሓዲያን ለአማንያን ያላቸው ጥላቻ ሁልጊዜም በመሆኑ አማንያን በያሉበት ተንኮላቸውን ነቅተው ሊጠነቀቁ እንደሚገባ፤
3. አላህ አማንያን ባሮች የሚረዳና ከከሓዲያን የሚበቀል መሆኑን፤
4. ቁርኣን ከመጨመርና ከመቀነስ የፀዳ ማንም ሊለውጠውና ሊበርዘው የማይችል የመፅሐፍቶች ሁሉ ዋና ምርጥ መፅሐፍ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የቡሩጆች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (86)
## የሌሊት መጭው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል ጧሪቅ)

سُورَةُ الطَّارِقِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (17) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلسَّمَآءِ وَٱلطَّارِقِ ۝١ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلطَّارِقُ ۝٢ ٱلنَّجۡمُ ٱلثَّاقِبُ ۝٣

**1-3.** በሰማዩ እና በሌሊት መጪውም እምላለሁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሌሊት መጪው ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ? ጨለማውን ሰንጣቂ ኮከብ ነው።

ከሌሊት መጪው ምዕራፍ (1-3) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረደቡት ምክንያት፡- የነብዩ (ﷺ) አጎት አቡጣሊብ ቂጣና ወተት ይዘው ወደ ነብዩ አጠገብ በመጡበት አንድ ኮኮብ ወደቀ ከዚያም አጠገባቸው የነበረውን እሳት ሞላው። እሳቸዉም ይህ ነገር ምንድን ነው ብለው ሲጠይቁ ይህ ከአላህ ከተወረወሩ ተዐምራቶች አንዱ ነው ሲሏቸው በጣም ስለተገረሙ ነው። (ዋሒዲ)

إِن كُلُّ نَفۡسٖ لَّمَّا عَلَيۡهَا حَافِظٞ ۝٤ فَلۡيَنظُرِ ٱلۡإِنسَٰنُ مِمَّ خُلِقَ ۝٥
خُلِقَ مِن مَّآءٖ دَافِقٖ ۝٦ يَخۡرُجُ مِنۢ بَيۡنِ ٱلصُّلۡبِ وَٱلتَّرَآئِبِ ۝٧

**4-7.** ነፍስ ሁሉ በእርሷ ላይ ጠባቂ ያለባት እንጂ ሌላ አይደለችም። የሰው ልጅ ከምን እንደተፈጠረ ይመልከት፤ ከተስፈንጣሪ ውሃ (የዘር ፈሳሽ) ተፈጠረ። ከጀርባና ከእርግብግቢቶች መካከል የሚወጣ ከሆነ የዘር ፈሳሽ ውሃ።

إِنَّهُۥ عَلَىٰ رَجۡعِهِۦ لَقَادِرٞ ۝٨ يَوۡمَ تُبۡلَى ٱلسَّرَآئِرُ ۝٩ فَمَا لَهُۥ مِن قُوَّةٖ وَلَا نَاصِرٖ ۝١٠
وَٱلسَّمَآءِ ذَاتِ ٱلرَّجۡعِ ۝١١ وَٱلۡأَرۡضِ ذَاتِ ٱلصَّدۡعِ ۝١٢

**8-12.** አላህ እርሱን በመመለሱ ላይ በእርግጥ ቻይ ነው። ሚስጥሮች በሚገለፁበት ቀን፤ (ለሰው) ምንም ኃይልና ረዳት አይኖረውም። የመመለስ ባለቤት (ዝናባማ) በሆነችው ሰማይ እምላለሁ። (በበቃይ) የመሰንጠቅ ባለቤት በሆነችው ምድርም እምላለሁ።

ከሌሊት መጪው ከ (5-10) ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፡- አቡል አሹድ የተባለ ሰውየ በቆዳ ላይ ይቆምና ከዚህ እኔን የገፈተረ ይህን ያህል ሽልማት እሰጠዋለሁ እያለ ከመፎከሩም አልፎ ሙሐመድ (ﷺ) የገሀነም ዘበኞች አስራ ዘጠኝ ናቸው ይላልና እናንተ ለዘጠኞቹ ሁኑ እንጂ እኔ አስሮችን እበቃቸዋለሁ ይል ስለ ነበር ነው። (ሱዩጢ)

إِنَّهُۥ لَقَوۡلٞ فَصۡلٞ ١٣ وَمَا هُوَ بِٱلۡهَزۡلِ ١٤

**13-14.** እርሱ (ቁርኣን)፤ እውነትን ከውሸት የሚለይ የአላህ ቃል ነው። እርሱም ቀልድ አይደለም። (ብየ እምላለሁ)።

إِنَّهُمۡ يَكِيدُونَ كَيۡدٗا ١٥ وَأَكِيدُ كَيۡدٗا ١٦ فَمَهِّلِ ٱلۡكَٰفِرِينَ أَمۡهِلۡهُمۡ رُوَيۡدَۢا ١٧

**15-17.** እነርሱ በእርግጥ ተንኮልን ያሴራሉ (ይሸርባሉ)። እኔ ተንኮልንም እመልሳለሁ (አመክናለሁ)። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ከሓዲያንን ቀን ሰጣቸው። ጥቂትን ጊዜ አቆያቸው (ታገሳቸው)።

**ከሌሊት መጪው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-17) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የመጀመሪያውን መነፋት የሚቀድሙ ልዩ ልዩ ክስተቶች እንዳሉ፤
2. መጥፎ ነገርን መጀመር ምን እንደሚያስከትል፤
3. እንዳንዱ ሰው ጋር ሁለት መላኢኮች እንዳሉና መልካም ስራውም ሆነ መጥፎ ስራው እንደሚፃፍ፤
4. የሰው ልጆች ለሁለት እንደሚከፈሉ የጀነት ወይም የጀሀነም መሆን፤
5. የቂያማ ዕለት ሰው ልጆችን የማንም ሽምግልናና ወዳጅነት ከአላህ ፈቃድ ውጭ የማይጠቅማቸው መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የአጥጧሪቅ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (87)
## የበላይ አሸናፊው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-አዕላ)

## سُورَةُ الأَعۡلَى

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (19) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

سَبِّحِ ٱسۡمَ رَبِّكَ ٱلۡأَعۡلَى ١ ٱلَّذِي خَلَقَ فَسَوَّىٰ ٢ وَٱلَّذِي قَدَّرَ فَهَدَىٰ ٣
وَٱلَّذِيٓ أَخۡرَجَ ٱلۡمَرۡعَىٰ ٤ فَجَعَلَهُۥ غُثَآءً أَحۡوَىٰ ٥

**1-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የዚያን ከሁሉ በላይ የሆነውን ጌታህን ስም አውሳ (አጥራ፣ አሞግስ)። የዚያን ሁሉን ነገር የፈጠረውንና ያስተካከለውን፤ የዚያን የወሰነውን ነገር ሁሉ ለተፈጠረለት የመራውን፤ የዚያን ግጦሽን ለምለም አርጎ ያወጣውን፤ ያበቀለውንና ከዚያ ደረቅና ጥቁር ያደረገውን (አምላክ ስም አሞግስ)።

سَنُقۡرِئُكَ فَلَا تَنسَىٰٓ ٦ إِلَّا مَا شَآءَ ٱللَّهُۚ إِنَّهُۥ يَعۡلَمُ ٱلۡجَهۡرَ وَمَا يَخۡفَىٰ ٧ وَنُيَسِّرُكَ
لِلۡيُسۡرَىٰ ٨ فَذَكِّرۡ إِن نَّفَعَتِ ٱلذِّكۡرَىٰ ٩

**6-9.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቁርኣንን በእርግጥ እናስነብብሃለን፤ አትረሳምም፤ አላህ ከፈለገው ነገር በስተቀር እናም እርሱ ግልፁንም የሚሸሸገውንም ሁሉ ያውቃልና፤ ለገሪቱም ሕይወት እስላምን ትከተል ዘንድ እናገራሃለን። ግሳፄይቱ ብትጠቅም ሰዎችን ገስፅም።

سَيَذَّكَّرُ مَن يَخۡشَىٰ ١٠ وَيَتَجَنَّبُهَا ٱلۡأَشۡقَى ١١ ٱلَّذِي يَصۡلَى ٱلنَّارَ ٱلۡكُبۡرَىٰ ١٢
ثُمَّ لَا يَمُوتُ فِيهَا وَلَا يَحۡيَىٰ ١٣ قَدۡ أَفۡلَحَ مَن تَزَكَّىٰ ١٤ وَذَكَرَ ٱسۡمَ رَبِّهِۦ فَصَلَّىٰ ١٥

**10-15.** አላህን የሚፈራ ሰው ሁሉ በእርግጥ ይገሰፃል። መናጢውም ይርቃታል። ያ! ታላቂቱን እሳት የሚገባውና፤ ከዚያ በእርሷ ውስጥ የማይሞትም

ህያውም የማይሆነው። የተጥራራ ሰው በእርግጥ ዳነ፤ የጌታውንም ስም ያወሳና የሰገደ።

بَلۡ تُؤۡثِرُونَ ٱلۡحَيَوٰةَ ٱلدُّنۡيَا ﴿١٦﴾ وَٱلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ وَأَبۡقَىٰٓ ﴿١٧﴾ إِنَّ هَٰذَا لَفِي ٱلصُّحُفِ ٱلۡأُولَىٰ ﴿١٨﴾
صُحُفِ إِبۡرَٰهِيمَ وَمُوسَىٰ ﴿١٩﴾

**16-19.** ይልቁንም ቅርቢቱን ሕይወት ትመርጣላችሁ፤ (ሰዎች ሆይ)፣ መጨረሻይቱ ሕይወት በላጭና፣ ዘወታሪ ስትሆን። (እናንተ ግን ይህችን ዐለም ትመርጣላችሁ)። ይህ መሆኑ በፊተኞቹ መጽሐፍት በኢብራሂምና በሙሳ መጽሐፍት ውስጥ የሰፈረ እውነታ ነው።

**ከበላይ አሸናፊው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-19) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ማስታወስ ግዴታ ስለ መሆን፤
2. የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ፤
3. ሰዎች ተግባራት ሁሉ ቀድመውኑ የተመዘገቡ ስለ መሆናቸው፤
4. የሰው ልጅ ከተስፈንጣሪ ፈሳሽ እንደመጣ ማስተማር፤
5. መጥፎን በውስጥ ደብቆ ተቃራኒውን ይፋ ከማውጣት ማስጠንቀቅ፤
6. የሰው ልጅ የትንሳኤ እለት ራሱን መርዳት እንደማይችልና ሌላንም መረዳት እንደማይገኝ፤
7. መጥፎን በውስጡ ደብቁ ተቃራኒውን ይፋ ማውጣት እንደማይገባና የሙቶ መነሳትን ሀቅነት ማረጋገጥ እንዳለብን፤
8. ከአላህ ዘንድ የመጡ ሁሉም እምነቶች እምነቶች አጠቃላይ ይዘትና መሰረታዊ ባህሪ አንድ ነው። በየትኛውም ዘመን የተላኩ ነብያት (عليهم السلام) ያስተላለፉት የነበረው መልዕክት ተመሳሳይ መሆን ከአንድ አላህ የተላኩ መሆናቸውን እንደሚያመለክት፤
9. ዱንያን አጣጥሎ አኼራን ማሞገስ፤ በዘካ፤ በዚክርና በሶላት ላይ ከፍተኛ ግፊት ማድረግ፤ አስፈላጊና ተገቢ መሆኑን፤
10. ነብዩ (ﷺ) የማይረሱ መሆናቸውን፤ ለገር ነገር ሁሉ የተገራላቸው መሆናቸውን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የበላዩ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (88)
## የሸፋኝቱ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አልጋሺየህ)

سُورَةُ الغَاشِيَةِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (26) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

هَلۡ أَتَىٰكَ حَدِيثُ ٱلۡغَٰشِيَةِ ١ وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٍ خَٰشِعَةٌ ٢ عَامِلَةٞ نَّاصِبَةٞ ٣
تَصۡلَىٰ نَارًا حَامِيَةٗ ٤ تُسۡقَىٰ مِنۡ عَيۡنٍ ءَانِيَةٖ ٥ لَّيۡسَ لَهُمۡ طَعَامٌ إِلَّا مِن ضَرِيعٖ ٦
لَّا يُسۡمِنُ وَلَا يُغۡنِي مِن جُوعٖ ٧

1-7. (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የሸፋኝቱ ትንሳኤ ወሬ መጣልህን? በዚያ ቀን የከሓዲያን ፊቶች ተዋራጆች ናቸው። ሰሪዎች* ለፊዎች ናቸው። የምታቃጥልን እሳት ይገባሉ። በጣም ከፈላች ምንጭም ይጋታሉ። ዶሪዕ ከሚባል (እሾሃማ) ዛፍ እንጂ ሌላ ምግብ የላቸውም። አካሉ የማያሰባ፤ ከረኃብም የማያብቃቃ ከሆነ፤

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «ከአላህ ሌላ ያሉትን ነገሮች እያመለከና እያጋራ የሞተ ሰው እሳት ውስጥ ገባ» አሉ።

وُجُوهٞ يَوۡمَئِذٖ نَّاعِمَةٞ ٨ لِّسَعۡيِهَا رَاضِيَةٞ ٩ فِي جَنَّةٍ عَالِيَةٖ ١٠ لَّا تَسۡمَعُ فِيهَا لَٰغِيَةٗ ١١
فِيهَا عَيۡنٞ جَارِيَةٞ ١٢ فِيهَا سُرُرٞ مَّرۡفُوعَةٞ ١٣ وَأَكۡوَابٞ مَّوۡضُوعَةٞ ١٤
وَنَمَارِقُ مَصۡفُوفَةٞ ١٥ وَزَرَابِيُّ مَبۡثُوثَةٌ ١٦

8-16. (የአማንያን) ፊቶች በዚያ ቀን ተቀማጣዮች ናቸው። በስራቸው ተደሳቾች ናቸው። በከፍተኛ ገነት ውስጥ ናቸው። በውስጧ ውድቅን ነገር አይሰሙም። በውስጧ ፈሳሾች ምንጮች አሉ። በውስጧ ከፍ የተደረጉ አልጋዎች አሉ። በተርታ የተኖሩ ብርጭቆዎችም፤ የተደረደሩ መከዳዎችም፤ የተነጠፉ ስጋጃዎችም (አሉ)።

أَفَلَا يَنظُرُونَ إِلَى ٱلْإِبِلِ كَيْفَ خُلِقَتْ ﴿١٧﴾ وَإِلَى ٱلسَّمَآءِ كَيْفَ رُفِعَتْ ﴿١٨﴾
وَإِلَى ٱلْجِبَالِ كَيْفَ نُصِبَتْ ﴿١٩﴾ وَإِلَى ٱلْأَرْضِ كَيْفَ سُطِحَتْ ﴿٢٠﴾

**17-20.** (ከሓዲያን) ግመል እንዴት እንደተፈጠረች አይመለከቱምን? ሰማይም እንዴት ከፍ እንደተደረገች! ተራራዎችም እንዴት እንደ ተቸከሉ! ምድርም እንዴት እንደተዘረጋች (አይመለከቱምን?!)

ከሸፋኝቱ ምዕራፉ (17-20) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የጀነት ፀጋዎች በቁርኣን ሲነገር ከሓዲያን በጉዳዩ ስለተገረሙ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

فَذَكِّرْ إِنَّمَآ أَنتَ مُذَكِّرٌ ﴿٢١﴾

**21.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አስታውስም። አንተ አስታዋሽ ብቻ ነህና።

لَّسْتَ عَلَيْهِم بِمُصَيْطِرٍ ﴿٢٢﴾

**22.** በእነርሱ ላይ አስገዳጅ (ተሿሚ) አይደለህም፤

إِلَّا مَن تَوَلَّىٰ وَكَفَرَ ﴿٢٣﴾ فَيُعَذِّبُهُ ٱللَّهُ ٱلْعَذَابَ ٱلْأَكْبَرَ ﴿٢٤﴾

**23-24.** ግን ከእውነት የዞረና የካደ ሰው፤ አላህም ታላቁን ቅጣት ይቀጣዋል።

إِنَّ إِلَيْنَآ إِيَابَهُمْ ﴿٢٥﴾ ثُمَّ إِنَّ عَلَيْنَا حِسَابَهُم ﴿٢٦﴾

**25-26.** መመለሻቸው ወደ እኛ ብቻ ነው። ምርመራቸውም በእኛ ላይ ብቻ ነው።

**ከሸፋኝቱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-23) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ስለ ሙቶ መነሳትና ስለ ምንዳ፤
2. ስለ ቂያማ ቀንና ከስሞቹ አንዱ ጋሺያህ መባሉ፤
3. ጀነት ውስጥ ልፋት እንደሌለ ሁሉ ገሀነም ውስጥ ከፍተኛ ልፋት መኖሩን፤
4. ሰዎች ሞራል ከሚነኩ ነገሮች ያልሆኑ ወሬዎች ናቸው።
5. ሙቶ መነሳት ያለ መሆኑን፤
6. የሰዎች መጨረሻ ማንም ይሁን ምንም ወደ አላህ መሆኑን፤
7. በጀነት ውስጥ ልፋት እንደሌለ እና ገሀነም ውስጥ ልፋት ስለመኖሮ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የሸፋኝይቱ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (89)
## የጎህ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ፈጅር)

سُورَةُ الفَجرِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (30) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلۡفَجۡرِ ١ وَلَيَالٍ عَشۡرٖ ٢ وَٱلشَّفۡعِ وَٱلۡوَتۡرِ ٣ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَسۡرِ ٤
هَلۡ فِي ذَٰلِكَ قَسَمٞ لِّذِي حِجۡرٍ ٥

**1-5.** በጎህ፤*1 እምላለሁ በአስር ሌሊቶችም፤*2 በጥንዱም*3 በነጠላውም፤ በሌሊቱም በሚሄድበት ጊዜ እምላለሁ። በዚህ መሀላ ለባለ አእምሮ ታላቅ መሀላ አለበትን?

*1 የሱብህ ሶላት ወይም ንጋቱ እራሱ ማለት ነው።

*2 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በዙልሒጃህ ወር የመጀመሪያዎቹ አስርቱ ቀናት ውስጥ ከሚሰሩት ስራዎች የበለጠ ስራ የለም» ሰዎችም «በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግልም?» አሏቸው እሳቸውም «በአላህ መንገድ ላይ የሚደረግ ትግልም ቢሆን ዳሩ ግን በአላህ መንገድ ላይ በሚደረግ ትግል ሕይወቱንና ገንዘቡን ለአላህ ሲል አደጋ ላይ ጥሎ ካለ አንዳች ነገር የማይመለስ ካልሆነ በስተቀር» አሉ»

የዙልሒጃህ ወይም የሙሐረም ወይም የረመዷን አስር ቀኖች ማለት ሊሆን ይችላል ይላሉ የተፍሲር ሙሁሮች።

*3 በጥንዱም ፍጡር ሁሉ ማለትን ይመርጣሉ ብዙ ምሁራን ምክንያቱም ፍጡር ተብሎ ጥንድ ያልሆነ አንድም የለምና።

أَلَمۡ تَرَ كَيۡفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِعَادٍ ٦ إِرَمَ ذَاتِ ٱلۡعِمَادِ ٧ ٱلَّتِي لَمۡ يُخۡلَقۡ مِثۡلُهَا فِي ٱلۡبِلَٰدِ ٨
وَثَمُودَ ٱلَّذِينَ جَابُواْ ٱلصَّخۡرَ بِٱلۡوَادِ ٩ وَفِرۡعَوۡنَ ذِي ٱلۡأَوۡتَادِ ١٠ ٱلَّذِينَ طَغَوۡاْ فِي
ٱلۡبِلَٰدِ ١١ فَأَكۡثَرُواْ فِيهَا ٱلۡفَسَادَ ١٢

**6-12.** ጌታህ በዓድ ህዝቦች ላይ እንዴት እንደሰራ አላወክምን?. አላየህምን? በኢረም፣ የባለ ረዣዥሚቱ አዕማድ፤ በዚያች ብጤዋ በአገሮች ውስጥ ያልተፈጠረ በሆነችው፤ በእነዚያ (በሸለቆዎችም) ቋጥኝን የቆረጡት በሆኑት

በሰሙድም፤ ባለ ችካሎች ፐራሜድ ባለ ብዙ ሰራዊት በሆነው ፈርዖንም፤ በእነዚያ በአገሮች ላይ ግፍ የሰሩ፤ በእርሷም ውስጥ ጥፋትን ያበዙ በሆኑት (እንዴት እንደሰራ አታውቅምን?)

فَصَبَّ عَلَيۡهِمۡ رَبُّكَ سَوۡطَ عَذَابٍ ﴿١٣﴾ إِنَّ رَبَّكَ لَبِٱلۡمِرۡصَادِ ﴿١٤﴾

**13-14.** በእነርሱ ላይም ጌታህ የቅጣትን አለንጋ አወረደባቸው፡፡ ጌታህ በመጠባበቂያ ላይ ነውና፡፡

فَأَمَّا ٱلۡإِنسَٰنُ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ رَبُّهُۥ فَأَكۡرَمَهُۥ وَنَعَّمَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَكۡرَمَنِ ﴿١٥﴾
وَأَمَّآ إِذَا مَا ٱبۡتَلَىٰهُ فَقَدَرَ عَلَيۡهِ رِزۡقَهُۥ فَيَقُولُ رَبِّيٓ أَهَٰنَنِ ﴿١٦﴾

**15-16.** የሰው ልጅ ጌታው በሞከረው ጊዜ ባከበረውና ባጣቀመው ጊዜ ጌታየ አከበረኝ (አበለጠኝ) ይላል፡፡ በሞከረውና በእርሱ ላይ ሲሳዩን ባጠበበበት (ጊዜ) እንዲሁ ጌታየ አሳነሰኝ ይላል፡፡

كَلَّاۖ بَل لَّا تُكۡرِمُونَ ٱلۡيَتِيمَ ﴿١٧﴾ وَلَا تَحَٰٓضُّونَ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ﴿١٨﴾
وَتَأۡكُلُونَ ٱلتُّرَاثَ أَكۡلٗا لَّمّٗا ﴿١٩﴾ وَتُحِبُّونَ ٱلۡمَالَ حُبّٗا جَمّٗا ﴿٢٠﴾

**17-20.** ተከልከሉ ይልቁንም የቲምን አታከብሩም፤ ድሃንም በማብላት ላይ አትታዘዙም፤ የውርስንም ገንዘብ የመሰብሰብን አበላል (ያለአግባብ) ትበላላችሁን፤ ገንዘብንም ብዙን (አለቅጥ) ትወዳላችሁ፤

كَلَّآۖ إِذَا دُكَّتِ ٱلۡأَرۡضُ دَكّٗا دَكّٗا ﴿٢١﴾ وَجَآءَ رَبُّكَ وَٱلۡمَلَكُ صَفّٗا صَفّٗا ﴿٢٢﴾ وَجِاْيٓءَ يَوۡمَئِذِۭ
بِجَهَنَّمَۚ يَوۡمَئِذٖ يَتَذَكَّرُ ٱلۡإِنسَٰنُ وَأَنَّىٰ لَهُ ٱلذِّكۡرَىٰ ﴿٢٣﴾ يَقُولُ يَٰلَيۡتَنِي قَدَّمۡتُ لِحَيَاتِي ﴿٢٤﴾
فَيَوۡمَئِذٖ لَّا يُعَذِّبُ عَذَابَهُۥٓ أَحَدٞ ﴿٢٥﴾ وَلَا يُوثِقُ وَثَاقَهُۥٓ أَحَدٞ ﴿٢٦﴾

**21-26.** (ሰዎች ሆይ! ተዉ)፡፡ ታቀቡ፡፡ ምድር ደጋግማ በተንኮታኮተች ጊዜ፤ ጌታህ በመጣና* መላዕክትም በሰልፍ ሆነው በመጡ ጊዜ፤ ገሀነምም በዚያ ቀን በተመጣች ጊዜ በዚያ ቀን ሰው ሁሉ (ጥፋቱን በትክክል) ይገነዘባል፡፡ መገንዘብም ለርሱ ከየቱ? ወይ እኔ!፣ ምነው በሕይወቴ (መልካምን ስራ) ባስቀደምኩ ኖሮ ይላል፡፡ (ግና ማስተዋሱ ምን ይፈየደዋል)፡፡ በዚያ ቀንም የእርሱን አቀጣጥ የመሰለ አንድም አካል አይቀጣም፡፡ የእርሱንም፣ አሰተሳሰር አንድም አካል አያስርም፡፡

✷ ይህና ይህን መሰል የአላህን ባህሪና ስሞች የሚናገሩ የቁርአን አናቅጾችና ሐዲሶች ተፍሲር በተመለከተ አላህን ከማንም ከምንም ፍጡር ጋር ሳናመሳስልና አላህን ከጉድለት በማጥራት በሰለፎች ግንዛቤና አረዳድ እናስቀምጣለን እዚህ ላይ በጣም ልንጠነቀቅ የሚገባው ነገር ነኛ እንዴት? (ከይፍ?) እና ለምን? የሚሉ ጥያቄዎች ሁሉ በፍጹም የተከለከሉ ናቸው 2ኛ አላህ በማንም በምንም አይመሳሰልም በዚህ ዙሪያ በሰፊው ለመረዳት በሱረቱ አል አዕራፍ (54) አንቀጽ ላይ የተጻፈውን ማብራሪያ ተመልከት።

يَٰٓأَيَّتُهَا ٱلنَّفۡسُ ٱلۡمُطۡمَئِنَّةُ ﴿٢٧﴾ ٱرۡجِعِيٓ إِلَىٰ رَبِّكِ رَاضِيَةٗ مَّرۡضِيَّةٗ ﴿٢٨﴾
فَٱدۡخُلِي فِي عِبَٰدِي ﴿٢٩﴾ وَٱدۡخُلِي جَنَّتِي ﴿٣٠﴾

**27-30.** (ለአመነች ነፍስም)፡- አንቺ በአላህ የረካሺው ነፍስ ሆይ፣ ወዳጅ፤ ተወዳጅ ሆነሽ ወደ ጌታሽ ተመለሺ። ከዉድ ባሮቼም ጋር ተቀላቀይ። ወደ ገነቴንም ግቢ ትባላለች።

ከጎህ ምዕራፍ (27) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በሐምዛ ወይም በዑስማን ምክንያት ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (ሱዩጢ)

በነጣላውም አላህ ማለት ነው። ምክንያቱም በሁሉ ነገር ብቸኛ አምላክ እሱ ብቻ ነውና።

**ከጎህ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-30) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከዙልሂጃ ወር መጀመሪያ ላይ ያሉት አስር ቀናቶች ክብር፤
2. አላህ አመፀኞችን በማጥፋት ሳይሆው ሙቶ መነሳትንና ምንዳ ከፋይነትቱን የሚያረጋግጥ መሆኑን፤
3. አላህ ባሮቹን የሚጠባበቅ በመሆኑ ከስህተት እራሳቸውን እንዲጠበቁ ማስጠንቀቁ፤
4. የቲሞችን ማክበር ግዴታ መሆኑና ረሀብተኛን ማብላት ተገቢ ስለመሆኑ፤
5. ውርስ በአግባቡ መስጠት ግዴታ መሆኑ፤
6. የሰው ልጆችን መብት እስከመርገም የሚደርስ የገንዘብ ፍቅር መጥፎ መሆኑን፤
7. የቂያማ ቀንን ዝርዝር በማውሳት አይቀሬ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የጎህ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (90)
## የሀገር ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-በለድ)

سُورَةُ البَلَدِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (20) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

لَآ أُقۡسِمُ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ١ وَأَنتَ حِلُّۢ بِهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ٢ وَوَالِدٖ وَمَا وَلَدَ ٣
لَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ فِي كَبَدٍ ٤

**1-4.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ሁኔታው ከሓዲያን እንደሚሉት) አይደለም በዚህ አገር (በመካ)* እምላለሁ አንተ በዚህ አገር ሰፋሪ ስትሆን። በወላጂና በወለዳቸው ልጆችም (በአደምና በዘሮቹ) ሁሉ (እምላለሁ)። ሰውን ሁሉ በእርግጥ በልፋት ውስጥ ሆኖ ፈጠርነው።

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዐባስ እንዳስተላፉት የመካ ከተማ በተከፈተችበት ወቅት እንዲህ አሉ፡- «አላህ ይህችን ከተማ የተጠበቀች አድርጓታል። እሾሃማ ቁጥቋጦቿን ፈፅሞ አይቁረጡ። ደኖቿንም ፈፅሞ አይመናመኑ። የወደቁ ነገሮች ፈፅሞ አይነሱ። ይህ አንድ ሰው እንዲፈፅም በአደባባይ ካላዘዘ በስተቀር ነው»

أَيَحۡسَبُ أَن لَّن يَقۡدِرَ عَلَيۡهِ أَحَدٞ ٥ يَقُولُ أَهۡلَكۡتُ مَالٗا لُّبَدًا ٦ أَيَحۡسَبُ أَن لَّمۡ يَرَهُۥٓ
أَحَدٌ ٧ أَلَمۡ نَجۡعَل لَّهُۥ عَيۡنَيۡنِ ٨ وَلِسَانٗا وَشَفَتَيۡنِ ٩ وَهَدَيۡنَٰهُ ٱلنَّجۡدَيۡنِ ١٠

**5-10.** በእርሱ ላይ አንድም የማይችል መሆኑን ይጠረጥራልን? ብዙን ገንዘብ አጠፋሁ ይላል፤ አንድም ያላየው መሆኑን ያስባልን? ለእርሱ ሁለት አይኖችን አላደረግንለትንምን? አንድ ምላስንና ሁለት ከንፈሮችንም፤ ሁለትን (የመልካምና የመጥፎ መንገድን) መንገዶች አልመራነውምን?

فَلَا ٱقۡتَحَمَ ٱلۡعَقَبَةَ ١١ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡعَقَبَةُ ١٢ فَكُّ رَقَبَةٍ ١٣ أَوۡ إِطۡعَٰمٞ فِي يَوۡمٖ ذِي
مَسۡغَبَةٖ ١٤ يَتِيمٗا ذَا مَقۡرَبَةٍ ١٥ أَوۡ مِسۡكِينٗا ذَا مَتۡرَبَةٖ ١٦ ثُمَّ كَانَ مِنَ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ
وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلصَّبۡرِ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلۡمَرۡحَمَةِ ١٧ أُوْلَٰٓئِكَ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَيۡمَنَةِ ١٨

**11-18.** ዐቀበቱን አልወጣም፡፡ ዐቀበቲቱን መውጣት ማለት ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ? እርሱ ጫንቃን* መልቀቅ ነው፡፡ ወይም የረሀብ ባለቤት በሆነ ቀን (ረሀብተኛን) ማብላት፤ የዝምድና ባለቤት የሆነን የቲም፤ ወይም የዐፈር ባለቤት የሆነን ች ግረኛ ማብላት ነው፡፡ ከዚያ ከእነዚያ በአላህ ከአመኑትና በመታገስ ላይ አደራ ከተባባሉት ሰዎች ጋር መሆን ነው፡፡ እነዚያ (ይህንን የፈፀሙ) መዝገባቸውን በቀኝ እጃቸው የሚቀበሉ ናቸው፡፡

* የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «ማንኛውም ሰው ሙስሊም የሆነን ባሪያ ነፃ ካወጣ፤ እሱ የባሪያውን ሰውነት ከባርነት ነፃ በማውጣት ስላዳነው አላህ የሱንም ሰውነት ከእሳት ያድነዋል»

وَٱلَّذِينَ كَفَرُواْ بِـَٔايَٰتِنَا هُمۡ أَصۡحَٰبُ ٱلۡمَشۡـَٔمَةِ ١٩ عَلَيۡهِمۡ نَارٞ مُّؤۡصَدَةُۢ ٢٠

**19-20.** እነዚያ በአንቀፆቻችን የካዱ ሁሉ እነርሱ መዝገባቸዉን በግራ እጃቸው የሚቀበሉ ናቸው፡፡ ለእነርሱ ተብላ የተዘጋጀች እሳትም አለች፡፡*

* ይህን መሰል አረፍተ ነገሮችን በተመለከተ በአልቂያማህ ላይ በሰፊው ተብራርቷል፡፡ ወላጅ ማለት እዚህ አባታችን አደምን ነው፤ ልጆች የተባሉት ደግሞ ዘሮቹ ማለት ነው የሚለው ተፈሲር የተሻለ በመሆኑ እኔም ይህኑ መርጫለሁ፡፡ በባርነት የተያዘን ባሪያን ነፃ ማውጣት ማለት ነው፡

**ከሀገር ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-20) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ስለ መካና ስለ ነብዩ (ﷺ) ክብር መጠቆም፤
2. የአደምንና የመልካም ዝርያዎቹ በአላህ ዘንድ ያላቸውን ክብር ማሳየት፤
3. የሰው ልጅ ከተወለደ ጀምሮ እስከሚሞት የማያርፍና ከዚያም በአኼራ በጀነት ገብቶ እስከሚያርፍ ወይም በእሳት ገብቶ ዘለለማዊ ቅጣትን እስኪቀጣ ድረስ የማያባራበት ወይም ልፋቱ የማያቆም መሆኑን፤
4. የቂያማ ቀን ተራራ ሊታለፍ የሚችለው በኢማንና ለፊሰቢሊላህ ገንዘቡን በማውጣትና በኸይር በመመካከር መሆኑን፤
5. የአላህንና የረሱልን (ﷺ) ህግ በመጣስ የደፈሩ ሰዎች ፀፀታቸው ምን ያህል ብርቱ እንደሚሆን መግለፅ፤
6. በእምነት የፀናች ነፍስ ስትሞት ቀብር ስትቀሰቀስና መዝገቦች ሲበተኑ ምን ያህል ደስተኛ እንደምትሆን ማብሰር፤
7. ቁስ ወዳድነት አዲስ ነገር ሳይሆን ከ (1400) አመት በፊትም የነበረና በወቅቱ የነበሩ የመካ ከሓዲያን ቁስ ወዳዶች እንደ ነበሩ፤
8. ውርስን በአግባቡ ማከፋፈል ተገቢ መሆኑን፤
9. ሰዎች ንብረታቸውን በወንጀል ከማውጣት በኸይር ስራ እንዲያውሉት ግፊት ማሳደርን እንማራለን፡፡

በአላህ ፈቃድ የሀገር ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ፡፡

# ምዕራፍ (91)
# የፀሐይ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አሽ-ሽምስ)

سُورَةُ الشَّمْسِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (15) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلشَّمۡسِ وَضُحَىٰهَا ١ وَٱلۡقَمَرِ إِذَا تَلَىٰهَا ٢ وَٱلنَّهَارِ إِذَا جَلَّىٰهَا ٣ وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰهَا ٤ وَٱلسَّمَآءِ وَمَا بَنَىٰهَا ٥ وَٱلۡأَرۡضِ وَمَا طَحَىٰهَا ٦ وَنَفۡسٖ وَمَا سَوَّىٰهَا ٧ فَأَلۡهَمَهَا فُجُورَهَا وَتَقۡوَىٰهَا ٨

**1-8.** በፀሐይና በብርሃኗ፤ እምላለሁ በጨረቃም ፀሐይን በተከተላት ጊዜ፤ በቀንም ፀሐይን በገለፃት ጊዜ፤ በሌሊቱም ፀሐይን በሸፈናት ጊዜ፤ በሰማይ እና በገነባትም፤ በምድር እና በዘረጋትም፤ በነፍስም ባስተካከላትም አመጽዋንና ፍርሃቷንም ባሳወቃት (አምላክ በአላህ እምላለሁ)።

قَدۡ أَفۡلَحَ مَن زَكَّىٰهَا ٩ وَقَدۡ خَابَ مَن دَسَّىٰهَا ١٠

**9-10.** (ነፍስን) ከኃጢአት ያጠራት ሰው ሁሉ ፍላጎቱን በእርግጥ አገኘ። በኃጢአትም የሸፈናት ሰው ሁሉ በእውነት አፈረ (ከሰረ)።

كَذَّبَتۡ ثَمُودُ بِطَغۡوَىٰهَآ ١١ إِذِ ٱنۢبَعَثَ أَشۡقَىٰهَا ١٢ فَقَالَ لَهُمۡ رَسُولُ ٱللَّهِ نَاقَةَ ٱللَّهِ وَسُقۡيَٰهَا ١٣ فَكَذَّبُوهُ فَعَقَرُوهَا فَدَمۡدَمَ عَلَيۡهِمۡ رَبُّهُم بِذَنۢبِهِمۡ فَسَوَّىٰهَا ١٤ وَلَا يَخَافُ عُقۡبَٰهَا ١٥

**11-15.** ሰሙድ ወሰን በማለፍዋ ምክንያት አስተባበለች፤ ጠማማዋ በተንቀሳቀሰ ጊዜ። ለእነርሱም የአላህ መልዕክተኛ (ሷሊህ)፦ የአላህን ግመልና የመጠጥ ተራዋን (ጠብቁላት) አላቸው። እነርሱ አስተባበሉትም፤ ከዚያ ወጓት፤ በኃጢአታቸውም ምክንያት ጌታቸው (ቅጣትን) በእነርሱ ላይ ደመደመባቸው፤ አስተካከላትም። አላህ (የምታስተካክለውን) ፍፃሜዋንም አይፈራም።

**ከፀሐይ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-15) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. መለኮታዊ ሀያልነቱን የገለፀባቸወን ሁኔታዎች ማየት፤
2. የሰው ልጅ ነፃ የሚወጣበትን ቀና መንገድና የሚከስርበትን የጥፋት ጉዞ መግለፅ፤
3. በእምነትና በመልካም ስራዎች ግፊት ማሳደርና በአንፃሩም ከሽርክና ከመጥፎ ስራዎች ማስፈራራት፤
4. የሰው ልጅ ከእሳት ነፃ ሆኖ ጀነት የመግባት እድሉን የሚወሰነው ራሱን ከወንጀሎች በማፅዳቱ ሲሆን የመከሰሩ ምክንያትም ራሱን በሽርክና በወንጀል በማቆሸሹ መሆኑን፤
5. የሰው ልጅ ነፃ የሚወጣበት መንገድ ትክክለኛ እምነትና መልካም ስራ ሲሆን የሚከስርበትም ሺርክና መጥፎ ስራ መሆኑን፤
6. እነዚህ አናቅፅ አላህ ኃያልነቱን የገለፀባቸውን ሁኔታዎች ማየት እንደሚገባ፤
7. ከሓዲያን የነብያትን መልዕክት ማስተባበላቸው የተለመደ መሆኑን፤
8. ነብዩን ማፅናናት ቁረይሾች የፈፀሙት ሺርክና የዋሉት ግፍ መጨረሻ አስከፊ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የፀሐይ ምዕራ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (92)
## የሌሊት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ለይል)

سُورَةُ اللَّيْلِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (21) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلَّيۡلِ إِذَا يَغۡشَىٰ ۝١ وَٱلنَّهَارِ إِذَا تَجَلَّىٰ ۝٢ وَمَا خَلَقَ ٱلذَّكَرَ وَٱلۡأُنثَىٰٓ ۝٣
إِنَّ سَعۡيَكُمۡ لَشَتَّىٰ ۝٤

**1-4.** (ሰዎች ሆይ!) በሌሊቱ (ጨለማውን) በሚሸፍነው ጊዜ፤ በቀንም በተገለፀ ጊዜ፤ ወንድንና ሴትን በፈጠረውም (አምላክ) እምላለሁ። ስራችሁ በእርግጥ የተለያየ ነው ብየ፡ (እምላለሁ)

فَأَمَّا مَنۡ أَعۡطَىٰ وَٱتَّقَىٰ ۝٥ وَصَدَّقَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ۝٦ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡيُسۡرَىٰ ۝٧

**5-7.** ያ! ገንዘቡን የሰጠ ሰው ጌታውን የፈራና፤ በመልካሚቱ እምነት ያረጋገጠ ሰው ለመልካም ነገር ሁሉ እናዘጋጀዋለን።

وَأَمَّا مَنۢ بَخِلَ وَٱسۡتَغۡنَىٰ ۝٨ وَكَذَّبَ بِٱلۡحُسۡنَىٰ ۝٩ فَسَنُيَسِّرُهُۥ لِلۡعُسۡرَىٰ ۝١٠
وَمَا يُغۡنِي عَنۡهُ مَالُهُۥٓ إِذَا تَرَدَّىٰٓ ۝١١

**8-11.** ያ፣ በገንዘቡ የሰሰተ ሰው በራሱ የተብቃቃና በራሱ የተመካ በመልካሚቱ እምነት ያስተባበለም ሰው ለከፋ ተግባር ሁሉ እናዘጋጀዋለን። ገሀነም በወደቀ ጊዜ ያ፣ ገንዘቡ ከእርሱ ምንም አይጠቅመውም። አያድነውም።

إِنَّ عَلَيۡنَا لَلۡهُدَىٰ ۝١٢ وَإِنَّ لَنَا لَلۡأٓخِرَةَ وَٱلۡأُولَىٰ ۝١٣ فَأَنذَرۡتُكُمۡ نَارٗا تَلَظَّىٰ ۝١٤
لَا يَصۡلَىٰهَآ إِلَّا ٱلۡأَشۡقَى ۝١٥ ٱلَّذِي كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰ ۝١٦

**12-16.** ቅኑን መንገድ መግለፅ በእኛ ላይ ሃላፊነት አለብን። መጨረሻይቱም መጀመሪያይቱም ዓለም የእኛ ናቸው። እናም ጠማማ፤ በአላህ ያስተባበለና ከትዕዛዝ የሸሸ እድለ ቢስ በስተቀር የማይገባባትን የምትንቀለቀል እሳት አስጠነቀቅኳችሁ (በላቸው)።

وَسَيُجَنَّبُهَا ٱلۡأَتۡقَى ﴿١٧﴾ ٱلَّذِي يُؤۡتِي مَالَهُۥ يَتَزَكَّىٰ ﴿١٨﴾ وَمَا لِأَحَدٍ عِندَهُۥ مِن نِّعۡمَةٖ تُجۡزَىٰٓ ﴿١٩﴾
إِلَّا ٱبۡتِغَآءَ وَجۡهِ رَبِّهِ ٱلۡأَعۡلَىٰ ﴿٢٠﴾ وَلَسَوۡفَ يَرۡضَىٰ ﴿٢١﴾

**17-21.** ያ የሚጥራራ ሆኖ ገንዘቡን ለሰዎች የሚሰጥና፤ አላህን በጣም ፈሪ የሆነ በእርግጥ ይርቃታል። ለአንድም ሰው በእርሱ ዘንድ የሚመለስ ውለታ ሳይኖር።* የታላቁን ጌታውን የአላህን ውዴታ ለመፈለግ (ይህንን ስራ)። እርሱማ ወደ ፊት (የፈለገው ተስጥቶት) በእርግጥ ይደሰታል።

✶ ዐብደላህ ብን አቢ አውፋ የእነዚህ አናቅፅ የወረዱበት ምክኒያት በዚያ ስድስት ባሪዎችን በገንዘባቸው ገዝተው ነፃ ባወጡት ጀግና በአቡበክር ሲዲቅ ምክንያት ነው» ይላሉ።

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐሊይ ኢብኑ አቡጣሊብ ከአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ጋር አንድ ቀን ቁጭ ብለን ሳለን እንዲህ አሉ፦ «ከመካከላችሁ ውስጥ አንዱ መቀመጫው ከጀነት ይሁን ወይም ከእሳት ሳይፃፍለት የቀረ የለም» አሉ። እኛም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ታዲያ ስራዎቻችንን አቁመን በዚሁ እንመካ እንዴ?» አልናቸው። እሳቸው «በፍፁም ስራችሁንማ ተግታችሁ ስሩ ሁሉም ሰው ለሚሰሪው ቀላል ነው» ካሉን በኋላ «የሰጠ ሰውማ ጌታውን የፈራም፤ በመልካሚቱም እምነት ያረጋገጠ፤ ለገሪቱም ስራ እናሻጋግረዋለን። የሰሰተ ሰውማ የተብቃቃም በራሱ የተመካ በመልካሚቱ እምነት ያስተባበለም፤ ለክፉይቱ ስራ እናዘጋጀዋለን» (አል-ለይል 5-10) የሚለውን የቁርኣን አንቀፅ አነበቡ።

ከሌሊት ምዕራፍ ከ (1-21) ኛው ያሉት አናቅፅ የወረዱበት ምክንያት፦ ሱዲይ የተባለው ዓሊም እንደሚሉት ከመዲና አንሷሮች አንድ ሰውዩ የተምር አትክልት ነበረው። ከዛፎቹ የአንዱ ቅርንጫፍ በአንድ ድሃ አንሷሪ ቤት ተንዘርፍፎ ነበር። ባለ ሀብቱ ለመልቀም ሲፈለግ አንዳንድ ፍሬዎች በድህው ግቢ ሲወድቁ የድሀው ሰውዬ ልጆች እዬለቀሙ ሲበሉ ሰውየው ወርዶ ይቀማቸው ነበር። ከዚህም አልፎ በአፋቸው ውስጥ ያስገቡትን ሳይቀር እንኳን ጣቱን አስገብቶ ያስተፋቸው ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን ድሃው ሰው ይህን ችግር ለነብዩ (ﷺ) በዝርዝር ሲያስረዳቸው ነብዩ (ﷺ) ወደ ሰውየው በመሄድ ወደ ሰውየው ግቢ የገባቸውን የተምር ዛፍ ሰጥተኸን የጀነት የተምር ዛፍ ቢሰጥህ ስላሉት እኔ ብዙ የተምር እግሮች አሉኝ። ነገር ግን እንደዚህች የሚጣፍጥ ፍሬ ያላት ባለማግኘቴ ለማንም አልሰጥም አላቸው። ከዚያ ሰውየውም ወደ አቡ ደህዳህ ሄደና ነብዩን እንደሚሰማና እንደሚያከብራቸው ስለ አወቀ ነገረው። አቡደህዳህም ለነብዩ ሄዶ ለእሱ የሰጡትን ለእኔ ይሰጡኛል ከእሱ ልውሰዳት ሲላቸው አዎ አሉት። በዚህ ጊዜ ወደ ባለተምሩ ሄደና በዋጋ መደራደር ሲጀምር ሙሐመድ እኮ በጀነት የተምር ዛፍ ሰጥቶኝ ነበር እንቢ ብየው ነው ሲለው መሸጥ ትፈልጋለህ አለው። እሱም በፍፁም ከመጠን በላይ የሚያጓጓ ዋጋ ካልተሰጠሁ በስተቀር አለው። ስንት ማለት ነው በማለት ጠየቀው። አርባ የተምር እግር ነዋ አለው። መለስ አድርጎ በጣም አስወደድከው ብሎ ካሰበበት በኋላ በል በዚሁ ዋጋ ተቀብያለሁና አስመስክርልኝ በማለት ሲጠይቀው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው። (አል ቁርጡቢ)

**ከሌሊት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-21) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. የአላህን ትልቅነትና ግርማ ሞገስ መግለፅ፤
2. የሰው ልጅ ለተፈጠረለት ነገር የተገራ መሆኑንና ስለ ቀድር ግልፅ አስተምህሮ፤
3. ለኸይር ስራ መታደል የአላህ መሻት ጋር የሰው ልጆች ፍላጎትና ጉጉት ላይ የተመሰረተ መሆኑንና ለመጥፎ ስራ መጋለጥም እንዲሁ በራሳችን ምክኒያት እንደሆነ፤
4. ዱንያም ሆነ አኼራ የአላህ ብቸኛ ስልጣን መሆናቸውንና ሁለቱም መጠየቅ ያለባቸው ከእሱ ብቻ መሆኑን፤
5. የአቡበክር ሲዲቅን ወደር የለሽ ክብርና በጀነት መበሰራቸዉን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የሌሊት ምዕራ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (93)
# የረፋድ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አድዱሃ)

سُورَةُ الضُّحَىٰ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (11) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلضُّحَىٰ ۝١ وَٱلَّيۡلِ إِذَا سَجَىٰ ۝٢ مَا وَدَّعَكَ رَبُّكَ وَمَا قَلَىٰ ۝٣
وَلَلۡأٓخِرَةُ خَيۡرٞ لَّكَ مِنَ ٱلۡأُولَىٰ ۝٤ وَلَسَوۡفَ يُعۡطِيكَ رَبُّكَ فَتَرۡضَىٰٓ ۝٥

**1-5.** በረፋድ፤ በሌሊትም ፅጥ*[1] ባለ ጊዜ እምላለሁ። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ አላሰናበተህም፤ አልጠላህምም። መጨረሻይቱም ዓለም ከመጀመሪያይቱ ይልቅ ለአንተ በላጭ ናት።*[2] ጌታህ ወደ ፊት (ብዙ ስጦታ) በእርግጥ ይሰጥሃል። ከዚያ ትደሰታለህ።

✶1 የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ለይላ እንዳስተላለፉት ኡሙ ሃኒ ብቻ እንደነገረችን የመካ ከተማ በተከፈተች ጊዜ ነብዩ (ﷺ) እሷ ቤት ሰውነታቸውን ታጥበው ስምንት ረከዓት ሶላት ሰገዱ፤ ኡሙ ሃኒ እንዳለች «ነብዩ እንደዚህች ያለች ቀለል ያለች ሩኩዕና ሱጁዷ የተሟላች ሶላት ሰግደው አይቼ አላውቅም» ብላለች።

በሌላ ዘገባ አቡሁረይራህ እንዳስተላለፉት «(ነቢዩ) ወዳጅ ሶስት ነገሮችን አደራ ብለውኛል። እነሱም፡-

1. ከየወሩ ሶስት ቀን መፆምን፤
2. የ«አድዱሓ» ሶላት ሁለት ረከዓዎች መስገድን፤
3. ከመተኛቴ በፊት ዊትር መስገዴን» (ቡኻሪ ዘግበውታል)

✶2 አዎ የመጨረሻው ዓለም ከዱንያ ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ ነው። ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «በጀነት ውስጥ የእያንዳንዳችሁ የአለንጋ ቦታ ከዚች ዓለምና ከውስጧ ካሉት ይበልጣል» ብለዋል።

أَلَمۡ يَجِدۡكَ يَتِيمٗا فَـَٔاوَىٰ ۝٦ وَوَجَدَكَ ضَآلّٗا فَهَدَىٰ ۝٧ وَوَجَدَكَ عَآئِلٗا فَأَغۡنَىٰ ۝٨

**6-8.** የቲም ሆነህ አላገኘህምና አላስጠጋህምን? (አስጠግቶሃል)። የሳትክም ሆነህ አገኘህና መራህ። ደሃም ሆነህ አገኘህና አከበረህ።

فَأَمَّا ٱلۡيَتِيمَ فَلَا تَقۡهَرۡ ۝٩ وَأَمَّا ٱلسَّآئِلَ فَلَا تَنۡهَرۡ ۝١٠ وَأَمَّا بِنِعۡمَةِ رَبِّكَ فَحَدِّثۡ ۝١١

**9-11.** የቲምንማ አትጨቁን። ለማኙንም አትገላምጥ። የጌታህንም ፀጋ ግለፅ (አውራ)።

**ከረፋዱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-11) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ነብዩ (ﷺ) በሁለቱም ዓለም በጥሩ እንደተበሰሩ እና የሳቸው ተከታይ የሆነው ሁሉ የዚሁ እድል ባለቤት እንደሆነ፤
2. ኢስላም ለየቲም ያለውን እንክብካቤና ችግረኞችን በመርዳትም የሚጫወተውን ከፍተኛ ሚና መጠቆም፤
3. የአላህን ፀጋ ማመስገን እንዳለብን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የረፋዱ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (94)
## የልብ መስፋት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አሽ-ሸርህ)

سُورَةُ الشَّرۡحِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (8) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

أَلَمۡ نَشۡرَحۡ لَكَ صَدۡرَكَ ١ وَوَضَعۡنَا عَنكَ وِزۡرَكَ ٢
ٱلَّذِيٓ أَنقَضَ ظَهۡرَكَ ٣ وَرَفَعۡنَا لَكَ ذِكۡرَكَ ٤

**1-4.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ልብህን ለአንተ አላሰፋንልህምን? (አስፍተንልሀል) ያንን ጀርባህን ያከበደውን ሸክምህን አወረድንልህ መወሳትህንም ላንተ ከፍ አድርገንልሀል?

ከልብ መስፋት ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ካፊሮች ሙስሊሞችን በድህነት ሲያነውሯቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው የሚሉ አሉ። (ሱዩጢ)

فَإِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرًا ٥ إِنَّ مَعَ ٱلۡعُسۡرِ يُسۡرًا ٦
فَإِذَا فَرَغۡتَ فَٱنصَبۡ ٧ وَإِلَىٰ رَبِّكَ فَٱرۡغَب ٨

**5-8.** እናም ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አለ። ከችግር ጋር በእርግጥ ምቾት አለ። (የጀመርከውን ጥሩ ስራ) በጨረስክ በጨረስክም ጊዜ ሌላ ጥሩ ስራ ቀጥል (አስከትል)። (ሁልጊዜም) ወደ ጌታህ ብቻ ከጅል።*

* አላህን ከማምለክ ስትጨርስ ወደ ዱንያ ስራ ቀጥል

የሙስሊም ጠበብቶች ይህ አንቀፅ ዛሬ ዐለም እየተቸገረበት ያለዉን የስራ አጥነትን ችግር በአጩሩ የፈታ ነው ይላሉ። ምክንያቱም የሙስሊም ጊዜ መቼም ቢሆን እረፍት የለዉም። ከዱንያ ስራ ካረፈ ወደ አኺራ ስራ መጣጣር አለበትና። ኢብኑ መስዑድ«ከማንም ሰው የምጠላው ነገር ቢኖር የዲን ወይም የዱንያ ስራ ትቶ በከንቱ ጊዜን ማሳለፍን ነው» ብለዋል።

### ከልብ መስፋት ምዕራፍ ከ (1-8) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ

1. አላህ ነብዩን (ﷺ) ልባቸውን በመክፈት ወንጀላቸውን በመማርና ክብራቸውን ከፍ በማድረግ፤ የሙዕሚን ልብ ለዲን መከፈቱና ችግሮችን ለመሸከም መታደሉ ትልቅ ፀጋ መሆኑ፤

2. ሁልጊዜም ከችግር በስተኋላ የነገሮችን መቃለል እንዳለ ማስተማር፤
3. ዱንያ ከጭንቀትና ከችግር ሁልጊዜም ነፃ እንደማትሆን፤
4. የሰው ልጅም በችግር ጊዜ ትዕግስት እንዲኖረውና በደስታ ጊዜም አላህን ሊያመሰግን እንደሚገባው፤
5. ቀደም ሲልም የነበረበትን ችግርም ሆነ ተድላ ዘወር ብሎ ማስተዋል እንዳለበት፤
6. ይህን ሁሉ ፀጋ ስለለገሰው ጌታው አላህ ዘወትር ምስጋና ማድረስ ግዴታው ነው።
7. የነብዩ ሙሀመድ (ﷺ) ክብርና ማዕረግ ከፍ ያለ መሆኑን ከአንቀፆቹ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የልብ ማስፋት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (95)
## የበለስ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አት-ቲን)

سُورَةُ التِّينِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (8) ናቸው።

بِّسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

وَٱلتِّينِ وَٱلزَّيۡتُونِ ١ وَطُورِ سِينِينَ ٢ وَهَٰذَا ٱلۡبَلَدِ ٱلۡأَمِينِ ٣
لَقَدۡ خَلَقۡنَا ٱلۡإِنسَٰنَ فِيٓ أَحۡسَنِ تَقۡوِيمٖ ٤

**1-4.** በበለስና፣ በዘይቱን (ወይራ) ዛፍ፣ በሲንን ተራራና፣ በዚህ በፀጥተኛው (ፀጥታ በነገሰበት) አገር በመካ እምላለሁ። ሰውን በጣም በአማረ አቋም ላይ ፈጠርነው።

ثُمَّ رَدَدۡنَٰهُ أَسۡفَلَ سَٰفِلِينَ ٥ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ فَلَهُمۡ أَجۡرٌ غَيۡرُ
مَمۡنُونٖ ٦ فَمَا يُكَذِّبُكَ بَعۡدُ بِٱلدِّينِ ٧ أَلَيۡسَ ٱللَّهُ بِأَحۡكَمِ ٱلۡحَٰكِمِينَ ٨

**5-8.** ከዚያም (ከፊሉን) ከበታቾች ሁሉ በታች አድርገን መለስነው*። ግን እነዚያ በአላህ ያመኑትና መልካም ተግባራት የሰሩት ሲቀሩ ለእነርሱማ የማይቋረጥ ምንዳ አለላቸው። (የሰው ልጅ ሆይ) ታዲያ ከዚህ (እውነታ) በኋላ በፍርዱ ምን አስተባባይ አደረገህ? አላህ ከፈራጆች ሁሉ ይበልጥ ፈራጅ አይደለምን?

✶ አንዳንድ ዐሊሞች ሰው በማለት እዚህ ላይ የተፈለገው ሙቶ መነሳትን የካደ እንደ ወሊድ ኢብኑ ሙጊራህ ያሉትን ከሃዲ ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ የሰው ዘርን በሙሉ ለማለት ነው የተፈለገው ይላሉ።

### ከበለስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-8) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. የዘይቱንና የቲን ዛፎች፣ የሲና ተራራ፣ የመካ አካባቢዎች ያላቸውን ክብር፣
2. አላህ የሰውን ልጅ ባማረ ስብዕና በተሻለ ግንባታ በመፍጠሩ የዋለለትን ውለታ ማስታወስ፣
3. የሰው ልጅ የቱንም ያህል ቢዋብና ቢያምር ሄዶ ሄዶ ማርጀቱና መጃጀቱ እንደማይቀር፣
4. የሰው ልጅ ሲያረጅና ከእንቅስቃሴ ሲቋረጥ በወጣጥነቱ ይሰራው የነበረው መልካም ተግባር ምንዳ እንደሚቀጥልለት፣
5. በፍትህ ከአላህ የበለጠ ማንም እንደሌለ እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የበለስ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (96)
## የረጋ ደም ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ዐለቅ)

سُورَةُ العَلَقِ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (19) ናቸው።
### የሱረቱ አል ዓለቅ መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ሱረቱ ኢቅራእ፤ ሱረቱ አል ኢቅራእ ቢስሚረቢከ፤ ሱረቱ አል ኢቅራእ ወል ዐለቅ፤ ሱረቱ አልቀለም በመባልም ይታወቃል። ይህ ምዕራፍ ከቁርአኑ ምእራፎች ሁሉ በመጀመሪያ የወረደ ቢሆንም ማንበብና መፃፍ አስፈላጊ መሆኑን ያስተምራል። በተጨማሪም ያ! ሰውን ከዚያ ደካማ ከሆነ ፈሳሽ የፈጠረው ጌታ አላህ መማሪያና መግባቢያ የሆነውን መጻፍና እንዲሁም ያለወቃቸውን ነገሮች እንዲያስተምረው ያስገነዝባል። ሀብትና ጉልበት የአላህን ህግ እንዲጣስ ከሚገፋፉ ነገሮች መካከል መሆናቸውንና ሁሉም ወደ አላህ እንደሚለስ ያስታውስና ከአላህ መንገድ እንቅፋት የሆኑትን ሁሉ በማስፈራራት ቅንጥ ቅንጣቸውን በማስያዝ ወደ ገሀነም ሊያወርዳቸው እንደሚችል አስፍራርቶ በዚያ ዕለት ምንም ረዳት እንደማይኖር መክሮ የአላህን ህግ ለሚያስከብሩ ሁሉ አመፀኞችን እንደመስሉ ጥሪ በማስተላለፍ መልዕክቱን ያጠቃልላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱقۡرَأۡ بِٱسۡمِ رَبِّكَ ٱلَّذِي خَلَقَ ١ خَلَقَ ٱلۡإِنسَٰنَ مِنۡ عَلَقٍ ٢

**1-2.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በዚያ ሁሉን ነገር በፈጠረው ጌታህ ስም (ጀምርና) አንብብ። ሰውን ከረጋ ደም በፈጠረው (ጌታህ ስም)።

ٱقۡرَأۡ وَرَبُّكَ ٱلۡأَكۡرَمُ ٣ ٱلَّذِي عَلَّمَ بِٱلۡقَلَمِ ٤ عَلَّمَ ٱلۡإِنسَٰنَ مَا لَمۡ يَعۡلَمۡ ٥

**3-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) አንብብ። ጌታህ በጣም ቸር ሲሆን። ያ በብዕር ለሰው ልጅ ያላወቀውን ሁሉ ያሳወቀ ጌታ ሲሆን (አንብብ)።

كَلَّآ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَيَطۡغَىٰٓ ٦ أَن رَّءَاهُ ٱسۡتَغۡنَىٰٓ ٧ إِنَّ إِلَىٰ رَبِّكَ ٱلرُّجۡعَىٰٓ ٨

**6-8.** በእውነቱ የሰው ልጅ ራሱን የተብቃቃ (ባለ ሀብት) ሆኖ በማየቱ ምክንያት ወሰንን ያልፋል። መመለሻው ወደ ጌታህ ብቻ ነው።

ከረጋ ደም ከ (6) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- በአንድ ወቅት ያ! የዚህ ኡመህ ፈርዖን በመባል የሚታወቀው አቡ ጀህል ለህዝቦች በእውነት እያያችሁት ሙሐመድ ፊቱን በመሬት ላይ

ይደፋልን ብሎ ሲጠይቅ አዎ ሁል ጊዜ አይደል የሚሰግደው አሉት። እሱም እኔ እያ የሁት ካደረገ ግን አንገቱ ላይ እቆማለሁ። ወይም ፊቱን በአፈር ላይ አልሞሰምሰዋለሁ። አለና አንድ ቀን ነብዩ (ﷺ) እየሰገዱ ባሉበት ወቅት ያለዉን ሊተገብር ወደ እሳቸው መጥቶ ይህን ነገር ተው አላልኩህም? ሲላቸው ነብዩ (ﷺ) ስለ ተቆጡት በዚህ አገር አንድም ከእኔ የተሻለ ቡድን ያለው እንደሌለ ታውቃለህ። እንዴት ደፍረህ ትናገራለህ? አላቸው በዚህ ላይ እያለ ራሱን መቆጣጠር በማይችልበት መልአክ ፊት ለፊቱ ቆሞ ሲያስፈራራው ወደ ኋላ ሲሸሽ ና በእጁ ሲከላከል ያዩት ሰዎች ምነው ብለው ሲተይቁት በኔና በሱ መካከል የእሳት ጉድጓድ ነበረ የሚያስፈራራ ነገርም ነበረ በማለት ተናገረ። ነብዩም ስለ ዚህ ነገር ሲናገሩ ወደኔ ቀርቦ በነበረ መላይኮች አካሎቹን በተከፋፈሏቸው ነበር ብለዋል። ይህን ታሪክ አስመልክቶ ነው እነዚህ አናቅፅ የወረዱት። (አህመድ፤ ሙስሊምና ሱዩጢ)

أَرَءَيۡتَ ٱلَّذِي يَنۡهَىٰ ﴿٩﴾ عَبۡدًا إِذَا صَلَّىٰٓ ﴿١٠﴾ أَرَءَيۡتَ إِن كَانَ عَلَى ٱلۡهُدَىٰٓ ﴿١١﴾
أَوۡ أَمَرَ بِٱلتَّقۡوَىٰٓ ﴿١٢﴾ أَرَءَيۡتَ إِن كَذَّبَ وَتَوَلَّىٰٓ ﴿١٣﴾ أَلَمۡ يَعۡلَم بِأَنَّ ٱللَّهَ يَرَىٰ ﴿١٤﴾

**9-14.** (የሰው ልጅ ሆይ!) ያንን ባሪያን በሰገደ ጊዜ የሚከለክለውን ሰዉየ አየህን? (እስቲ ንገረኝ) ተከልካዩ ባሪያየ በትክክል መንገድ ላይ ቢሆን፤ ወይም (ፈጣሪውን) በመፍራት ቢያዝ ምን እንደሚሆን አየህን? (እስቲ ንገረኝ) ከልካዩ ቢያስተባብልና ከእምነት ቢሸሽ፤ አላህ የሚያይ መሆኑን አያውቅምን?

كَلَّا لَئِن لَّمۡ يَنتَهِ لَنَسۡفَعَۢا بِٱلنَّاصِيَةِ ﴿١٥﴾ نَاصِيَةٖ كَٰذِبَةٍ خَاطِئَةٖ ﴿١٦﴾
فَلۡيَدۡعُ نَادِيَهُۥ ﴿١٧﴾ سَنَدۡعُ ٱلزَّبَانِيَةَ ﴿١٨﴾

**15-18.** ይታቀብ፤ ባይከለከል አናቱን ይዘን እንጎትተዋለን። ያቺን ውሸታምና ስህተተኛ የሆነችውን አናቱን። ሸንጎውንም* ይጥራ፤ እኛም ዘበኞቻችንን እንጠራለን።

* ቡድኑን፤ አጋሮቹን፤ ደጋፊዎቹን እንደማለት ነው።

كَلَّا لَا تُطِعۡهُ وَٱسۡجُدۡ وَٱقۡتَرِب ۩ ﴿١٩﴾

**19.** ይታቀብ፤ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ይህን ለሚል ከሓዲ አትታዘዘው፤ ስገድ፤ ወደ አላህም ተቃረብ።

**ከረጋ ደም ምዕራፉ ከ (1-19) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ስለ ወህይ አጀማመርና የነብዩ (ﷺ) ነብይነት እንዴት እንደተከሰተና እንዴት እንደተጀመረ፤
2. መልካም የተባለን ሁሉ በአላህ ስም የመጀመር ምንዳ ምን ያህል አስፈላጊ መሆኑን፤
3. በመህፀን ውስጥ የሰው ልጅ ሺል እድገትን በተመለከተ ሰፊ መግለጫ፤
4. የአላህ ቸርነት ከሁሉ የበለጠ መሆኑ፤

5. ስለ መፃፍና ስለ መፃፊያ በዚህ በጨለመ ዘመን ማስታወሱና ክብር የሚገባው መሆኑን መጠቆም፤
6. አላህ የሰውን ልጅ የማያውቀውን በማሳወቁ የዋለለትን ከፍተኛ ውለታ ማስታወስና ማመስገን እንደሚገባ፤
7. የሰው ልጅ ባህሪ እምነት ከሌለው ምን እንደሚመስል፤
8. አላህ መልዕክተኛውን ሙሐመድ (ﷺ) በገሀድ እንደሚረዳ ቃል መግባቱን፤
9. ነብዩን (ﷺ) ከሁሉም በበለጠ ያሰያቃቸው የነበረውንና የዚህ ኡመት ፈርዑን ያሉትን አቡጀህልን አላህ እርግማን ያውርደበት መሆኑን በግልፅ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የረጋ ደም ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (97)
## የመወሰኛው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ቀድር)

سُورَةُ القَدْرِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፁ ብዛት (5) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِنَّآ أَنزَلۡنَٰهُ فِي لَيۡلَةِ ٱلۡقَدۡرِ ١ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ ٢

**1-2.** እኛ ቁርኣንን በመወሰኛው ሌሊት ውስጥ አወረድነው። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) መወሰኛው ሌሊት ምን እንደሆነ ምን አሳወቀህ?

ከመወሰኛው ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት:- ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አንድ ሺህ ወር ለጅሃድ መሳሪያ የተሸከመውን ሰው ታሪክ ስላወሩና ሰሀቦች በዚህ ሰውየ ተግባር ስለቀኑ እናንተም የዚህን ሰውየ እድል የምታገኙበት አለ ማለት ነው ብሎ ይህን አወረደ። (ሱዩጢ)

ሙሉው ቁርኣን የወረደው በነብዩ (ﷺ) የነብይነት እድሜ በ (23) አመት ውስጥ መሆኑ የታወቀ ሲሆን ይህ አንቀፅ ደግሞ ቁርኣን በለይለተል ቀድር መሆኑን ነው። እናም ቁርኣን በዚህ ሌሊት ከለውሐል መህፉዝ በአጠቃላይ ወደ ሰማዩ ዱንያ በአንድ ጊዜ የወረደ ሲሆን በዚያው ዕለት የመጀመሪያው ወደ ምድር ወረደ ማለት እንጂ ሁሉም ቁርኣን በአንድ ቀን ወደ መሬት ወረደ ማለት አይደለም በማለት ነው። ይህን ሌሊት ለይቶ ለማወቅ የተደረገው የሙሁራን ሙከራ ሁሉ ውጤታማ አልሆነም። ምክንያቱም (21) ኛው፤ (23) ኛው፤ (25) ኛው፤ (27) ኛው፤ (29) ኛው ነው በሚል የተፍሲር ሙሁራን የተለያዩ ሲሆን ሁሉም ለእንዳንዱ አባባል ማስረጃ ለማቅረብ ሙከራ አድርገዋል። ሆኖም በብዙሀኖቹ ዘንድ የተደገፈውና ማስረጃውም ጠንካራው አባባል (27) ኛው ወይም (21) ኛው ሌሊት ነው የሚሉት ናቸው። በአስሩ ሌሊቶች በሁሉም መፈለጉ ተገቢ ሲሆን በተለይ በነጠላ ቁትሮች ላይ ማተኮር እንዳለብን ነው።

لَيۡلَةُ ٱلۡقَدۡرِ خَيۡرٞ مِّنۡ أَلۡفِ شَهۡرٖ ٣ تَنَزَّلُ ٱلۡمَلَٰٓئِكَةُ وَٱلرُّوحُ فِيهَا
بِإِذۡنِ رَبِّهِم مِّن كُلِّ أَمۡرٖ ٤ سَلَٰمٌ هِيَ حَتَّىٰ مَطۡلَعِ ٱلۡفَجۡرِ ٥

**3-5.** መወሰኛው ሌሊት ከሺህ ወር በላጭ ናት። በእርሱ ውስጥ መላዕክትና ሩህ (ጂብሪል) በጌታቸው ፈቃድ ከነገሮች ሁሉ ይዘው ይወርዳሉ። እርሷ እስከ ጎህ መውጣት ድረስ* ሰላም ብቻ ናት።

✴ የአላህ መልዕክተኛ ስለ ዚህ ሌሊት ጉዳይ እንዲህ ብለዋል፦

1. «ለይለተል ቀድርን ከአላህ ምንዳ እንደሚያስገኝ አምኖ የቆመ፤ ያለፈ ወንጀሉ ይማርለታል»
2. የአላህ መልዕክተኛም...«የሁላችሁም ህልም በረመዷን የመጨረሻዎቹ ሰባት ቀናት ውስጥ በመሆኑ ላይ ተስማምቷል። ስለዚህም ለይለተል ቀድርን የሚፈልግ ሰው በመጨረሻዎቹ ሰባት ቀናት ውስጥ ይፈልጋት» አሉ። (ቡኻሪና ሙስሊም)
3. «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ለይለቱል ቀድር የትኛዋ ሌሊት እንደሆነች ባውቅ ምንድን ነው ማለት ያለብኝ?» በማት ጠየቅኳቸው። «አልላሁምመ ኢንነከ ዐፉውውን ቱሒብቡል ዐፉወ ወዕፉ ዐንኒይ፤ በይ» አሉኝ። ቲርሚዚ.
4. «ለይለተል ቀድርን በረመዷን ወር የመጨረሻዎቹ አስር ጎዶሎ ቀናት ውስጥ ፈልጓት» ቡኻሪ.

**ከመወሰኛው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናኘቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. ስለ ወህይና ስለ ነብይት ግልፅ አስተምህሮት፤
2. የቀዷና ቀደርን ጉዳይ በግልፅ ማሳየት፤
3. የለይለተል ቀድር ክብርና በእሷ ውስጥ የሚሰሩ ተግባራት ያላቸው ምንዳ በሌላው ጊዜ ከሚሰሩት ያላቸውን ብልጫ፤
4. ቁርአን መውረድ የጀመረው በረመዷን ወር ላይ መሆኑን፤
5. ቁርአንን መቅራትና መስማት ያለው ከፍተኛ ምንዳ ያለው መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የመወሰኛው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (98)
# የግልፅ አስረጂዋ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-በይናህ)

سُورَةُ البَيِّنَةِ

**የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (8) ናቸው።**

**የሱረቱ አል-በይናህ መግቢያ**

አነስ ብን ማሊክ እንደዘገቡት ነብዩ አንድቀን ለኡበይ አላህ በአንተ ላይ ለምየኩንንየሚለዉን የቁርኣንምዕራፍ እንድማር አዞኛል አሉት። ኡበይ እኔን ስሜን ጠርቶ አላቸው እሳቸዉም አዎ አሉት በዚህ ጊዜ አለቀሰ።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

لَمۡ يَكُنِ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ مُنفَكِّينَ حَتَّىٰ تَأۡتِيَهُمُ ٱلۡبَيِّنَةُ ١
رَسُولٞ مِّنَ ٱللَّهِ يَتۡلُواْ صُحُفٗا مُّطَهَّرَةٗ ٢ فِيهَا كُتُبٞ قَيِّمَةٞ ٣

**1-3.** እነዚያ ከመጽሐፍ ባለቤቶችና ከአጋሪዎች በአላህ የካዱት ሰዎች ግልፅ አስረጂ እስከ መጣላቸው ድረስ (ከነበሩበት አቋም) ተወጋጆች* አልነበሩም። (አስረጁም) ከአላህ የሆነ መልዕክተኛ፤ የተጥራሩ የተጥራሩን መጽሐፎች የሚያነብ ነው። በውስጧ ቀጥተኛ የሆኑ ፁሁፎች ያሉባት የሆነችን፤ (መጽሐፎች የሚያነብ ነው)።

✶ ተወጋጆች ከሚባል ይልቅ አልተተውም ብሎ መተርጎሙና ሐሳቡም መመሪያ ሳይላክላቸው አልተተዉም በሚል መልዕክት መረዳቱ የተሻለ ይሆናል። ምክኒያቱም አልተወገዱም ማለቱ ብዙ አስቸጋሪ ነገሮችን ያስከትላልና ነው። ይህ አባባል ክህደት በመፅሐፍ ሰዎች ዉስጥም ሆነ በአጋሪዎች ዘንድ እንዳለ በግልፅ ያሳያል።

وَمَا تَفَرَّقَ ٱلَّذِينَ أُوتُواْ ٱلۡكِتَٰبَ إِلَّا مِنۢ بَعۡدِ مَا جَآءَتۡهُمُ ٱلۡبَيِّنَةُ ٤
وَمَآ أُمِرُوٓاْ إِلَّا لِيَعۡبُدُواْ ٱللَّهَ مُخۡلِصِينَ لَهُ ٱلدِّينَ حُنَفَآءَ وَيُقِيمُواْ ٱلصَّلَوٰةَ وَيُؤۡتُواْ ٱلزَّكَوٰةَۚ
وَذَٰلِكَ دِينُ ٱلۡقَيِّمَةِ ٥ إِنَّ ٱلَّذِينَ كَفَرُواْ مِنۡ أَهۡلِ ٱلۡكِتَٰبِ وَٱلۡمُشۡرِكِينَ فِي نَارِ جَهَنَّمَ
خَٰلِدِينَ فِيهَآۚ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ شَرُّ ٱلۡبَرِيَّةِ ٦

**4-6.** እነዚያም መጽሐፉን የተሰጡት ሰዎች ግልፅ አስረጂ ከመጣላቸው በኋላ እንጂ አልተለያዩም። አላህን ሃይማኖትን ለአላህ ብቻ አጥሪዎች፣ ቀጥተኞች ሆነው ሊግገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፤ ዘካንም በትክክል ሊሰጡ እንጂ ያልታዘዙ ሲሆን (ተለያዩ)። ይህም የቀጥተኛይቱ ሃይማኖት ድንጋጌ ነው። እነዚያ ከመጽሐፍ ሰዎችና የካዱ ሰዎች አጋሪዎችም በውስጧ ዘውታሪዎች ሲሆኑ በገሀነም እሳት ውስጥ ናቸው። እነዚያ እነርሱ ከፍጥረቱ ሁሉ መጥፎዎች እነርሱ ናቸው።

إِنَّ ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ أُوْلَٰٓئِكَ هُمۡ خَيۡرُ ٱلۡبَرِيَّةِ ٧
جَزَآؤُهُمۡ عِندَ رَبِّهِمۡ جَنَّٰتُ عَدۡنٖ تَجۡرِي مِن تَحۡتِهَا ٱلۡأَنۡهَٰرُ خَٰلِدِينَ فِيهَآ أَبَدٗاۖ
رَّضِيَ ٱللَّهُ عَنۡهُمۡ وَرَضُواْ عَنۡهُۚ ذَٰلِكَ لِمَنۡ خَشِيَ رَبَّهُۥ ٨

**7-8.** እነዚያ በትክክል ያመኑና መልካሞችን ተግባራት የሰሩ እነርሱ ከፍጥረት ሁሉ በላጭ (ምርጦች) ናቸው። በጌታቸው ዘንድ ምንዳቸው ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው መኖሪያ ገነቶች ናቸው። በውስጣቸው ለዘልዓለም ዘወታሪዎች ሲሆኑ ይገቡባቸዋል። አላህ ከእነርሱ ስራቸውን ወደደላቸው። ከእርሱም ምንዳውን ወደዱ። ይህ እድል ጌታውን ለፈራ ሰው ሁሉ ነው።

**ከግልፅ አስረጂዋ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-8) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. ኢስላም በመጣበት ዘመን የነበሩት ልዩ ልዩ እምነቶች የተለዋወጡና እውነትና ውሸት የተደባለቀባቸው እንደነበሩ፤
2. የመፅሐፍ ባለቤቶች የነብዩን መላክ በተስፋ ይጠብቁት እንደነበርና ሲላኩ ግን ከፊሎች አምነው ከፊሎቹ እንደካዱ፤
3. የመፅሐፍ ባለቤቶች በመፅሐፋቸው ከታዘዙት መካከል ሽርክና ኩፍርን ወደ ጎን በመተው አላህን በብቸኝነት እንዲያመልኩ፤ ሶላት እንዲሰግዱና ዘካ እንዲሰጡ ሲሆን ለምን ይህን ተግብሩ ሲባሉ አንደ አመፁ፤
4. ትክክለኛው እምነትና ነፃ የሚያወጣው መንገድ አላህን በብቸንነት ማምለክና ሶላት መስገድ ዘካ መስጠት መሆኑን፤
5. በኢስላም የካደ ሰው ምንዳው ከሁሉም የከፋ መሆኑን፤
6. ኢስላምን ተቀበሎ ምንዳው ጀነት እንደሆነ፤
7. አላህን መፍራት ምን ያህል መልካም ስነ ምግባር እንደሆነ፤
8. ከሓዲያን ካፊሮች ከከብቶችና ከእንሰሳዎች በታች መሆናቸውን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የግልፅ አስረጅዋ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (99)
# የመሬት መንቀጥቀጥ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አዝ-ዘልዘለህ)

سُورَةُ الزَّلۡزَلَةِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (8) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِذَا زُلۡزِلَتِ ٱلۡأَرۡضُ زِلۡزَالَهَا ١ وَأَخۡرَجَتِ ٱلۡأَرۡضُ أَثۡقَالَهَا ٢ وَقَالَ ٱلۡإِنسَٰنُ مَا لَهَا ٣
يَوۡمَئِذٖ تُحَدِّثُ أَخۡبَارَهَا ٤ بِأَنَّ رَبَّكَ أَوۡحَىٰ لَهَا ٥

**1-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ምድር በኃይል መንቀጥቀጥን በተንቀጠቀች ጊዜ፤ ምድር ሸክሞችዋን ባወጣችም ጊዜ፤ ሰውም ምን ሆነች ባለ ጊዜ፤ ጌታህ ለእርሷ በማሳወቁ ምክንያት። በዚያ ቀን ወሬዎቿን* ትናገራለች።

✴ በሷ ላይ የተሰሩትን መልካም ወይም መጥፎ ስራዎችን ማለት ነው።

يَوۡمَئِذٖ يَصۡدُرُ ٱلنَّاسُ أَشۡتَاتٗا لِّيُرَوۡاْ أَعۡمَٰلَهُمۡ ٦ فَمَن يَعۡمَلۡ مِثۡقَالَ ذَرَّةٍ خَيۡرٗا يَرَهُۥ ٧
وَمَن يَعۡمَلۡ مِثۡقَالَ ذَرَّةٖ شَرّٗا يَرَهُۥ ٨

**6-8.** በዚያ ቀን ሰዎች ሁሉ ስራዎቻቸውን እንዲያዩ ይደረጉ ዘንድ እንደየስራቸው የተበታተኑ ሆነው (ከየመቃብራቸው ወደ መቆሚያው ስፍራ) ይመለሳሉ። የብናኝ ክብደት ያህል መልካምን የሰራ ሰው ያገኘዋል።*1 የብናኝ ክብደት*2 ያህልም ክፉን የሰራ ሰው ያገኘዋል።

✴1 ዉድ ሙስሊሞች አዎ በዚያ ቀን ትንሽም ብትሆን መልካም ተግባር ትጠቅማለች። ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዲህ ብለዋል። የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ)፡- «አንድ ሰው በዕለተ ቂያማ ከተግባሮቹ መካከል መጀመሪያ የሚመረምረው ስለ ሶላቱ ነው። እርሷ ተስተካክላ ከተገኘች ነፃ ሆነ ከፈተናትም አለፈ። እርሷ ከተበላሸች ግን አፈረ፤ ከሰረ። ከግዴታ ድርጊቶች ውስጥ ጉድለት ከተገኘበት ኃያሉ አላህ «ባሪያዬ የጎደለበትን የግዴታ ተግባር የሚሞላለት ሱንና ተግባር እንዳለው ተመልከቱለት» በማለት ያዝዛል። ከዚያም ሌሎች ተግባራቱ ከዚሁ አኳያ ይቃኛሉ» ብለዋል።

የደግ ተግባርም ሆነ የመልካም ንግግር ትንሺም ቢሆን አይናቅም አይናቅም።

ነቢዩ በዚህ ጉዳይ ብዙ አስተምረዋል።

ሀ. ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አንዲት ሴት እስከትሞት ድረስ አስራ ባስቀመጠቻት ድመት ምክንያት እሳት ገብታለች። ይኸውም ባሰረቻት ጊዜ ያላበላቻትና ያላጠጣቻት ወይም የምድር ነፍሳት ትመገብ ዘንድ ያልለቀቀቻት በመሆኗ ነው»

ለ. ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «አንድ ዉሻ ውሃ ጥም ሊገለው በዉሃ ጉድጓድ አጠገብ እየዞረ ባለበት አንዲት የበኒ ኢስራኢል በመጥፎ ወንጀል ላይ እድሜዋን የፈጀች ሴት አይታው ጫማዋን አውልቃ ከጉድፏዱ አውጥታ ስለ አጠጣችው አላህ ወንጀሏን ማራት» ብለዋል።

የድመቷን ሐዲስ የተመለከቱ አንድ ዙህሪ የተባሉ ታላቅ ዐሊም«ይህ የሆነው ማንም ሰው እነዳይሰንፈና ሌላው ደግሞ ተሰፋ እንዳይቆርጥ ነው» ብለዋል።

ቢላል ኢብኑ ሰዕድ የተባለ ዐሊም «መመልከት ያለብህ የወንጀሉን ማነስ ሳይሆን የወነጀልከውን ማንነት ነው»ብለዋል።

ሐ. አቡ ዳውድ በዘገቡት ሐዲስ «እናታችን ዓኢሻ ስለ ሶፊያ አጭር መሆኗ በቂህ ነው ብለው ለነቢዩ ሲያሙ ነቢዩ በምድር ላይ ያሉት ውቅያኖሶችን ሊበክል የሚችል ቃል ተናገርሽ» በማለት አጭርን ሰው አጭረ ነው ብሎ ማንኳጠጡ እንኳን ምን ያህል ክብደት እንዳለው ነው።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ከመልካም ስራ ዉስጥ ምንንም አትናቅ ለወንድምህ ፈገግ ማለትን እንኳን» ብለዋል።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «አቡበርዘህ ነቢዩን የሚጠቅመኝን ነገር አስተምሩኝ ባለቸው ጊዜ ሙስሊሞችን የሚያስቸግርን ከመንገዳቸው ላይ አስወግድላቸው» ብለውታል።

ሙስሊም በዘገቡት«አንድ ሰው በመንገድ ላይ ሲያልፍ የዛፍ ቀንዘል በመንገድ ላይ ወድቆ ስላየ ይህን ዛፍ ከሙስሊሞች መንገድ ላይ አስወግዳለሁ በማለቱ ብቻ አላህ ማረው ብለዋል» እነዚህ መሰሎችን ኢስላማዊ ትምህርቶችን የሰሙ ሙስሊሞች ለሁሉም ማህበረሰብ መልካም አርአያ ሊሆኑ ይገባል።

✳2 ከመሬት መንቀጥቀጥ ከአንቀፅ (1-8) ያሉት አናቅፅ ጥቅል መልዕክት፡- የትንሳኤ ዕለት መሬት በመንቀጥቀጥ በውስጧ ያሉትን ሁሉ እንደምታወጣ እና በእሷ ላይ ምን ምን ይሰራበት እንደነበር እንደምትናገር ከዚያም ሂሳብ፤ ሚዛን፤ ምንዳ የሚባል ነገር እንዳለ ያስተምራል።

**ከመሬት መንቀጥቀጥ ምዕራፍ ከ (1-8) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የትንሳኤ ቀን መከራ ከባድ መሆኑንና ሁኔታዎች እንደሚለዋወጡ፤
2. የሰው ልጆች በዚች ዓለም በሰሩት ስራ ለለመመርመር እንደሚቀሰቀሱ፤
3. የሰው ልጅ መልካም ስራም ሆነ መጥፎ ተግባርን ትንሽ ነው በሚል መናቅ እንደሌለበትና ሁለተኛው ዓለም ከፍተኛ ዝግጅት እንደሚያስፈልገው ያሳያል።

## በአላህ ፈቃድ የመሬት መንቀጥቀጥ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (100)
## የሯጮች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ዓዲያት)

سُورَةُ العَادِيَاتِ

### የወረደው በመዲና ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (11) ናቸው።
### የሱረቱ አል ዓዲያት መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ወልዓዲያት በመባልም ይታወቃል። አማኝ በመጥፎ ተግባሩ በዱንያ ሲቀጣ መልካም ተግባሩ ደግሞ በመጀመሪያ የሰው ልጅ ለጌታው ፀጋ ከሀዲ መሆኑን አላህ በመሀላ አጠንክሮ እንዳስጠነቀቀ ያወሳና የሰው ልጅ ራሱ ይህን ተግባሩን የሚያውቅ ገንዘብ ስለሚወድ በጣም የሚጓጓ መሆኑን ካስተማረ በኋላ ሙቶ መነሳት የማይቀር ሐቅ ስለ መሆኑ በማውሳት መልዕክቱን ያጠቃልላል።

ኢብኑ አቢ ሓቲም ከኢብኑ ዐባስ እንደዘገቡት ከሆነ ነብዩ ወደ በኒ ኪናና አንድ የዘመቻ ቡድን ልከው ለወር ያክል ወሬያቸው ስለጠፋ ነው ነብዩን ለማፅናናት ይህን ምዕራፍ ያወረደው» ብለዋል። ሱዩጢ ከዐሊይ እንደዘገቡት ከሆነ ደግሞ እኒህ ፈረሶች የዘመቻ ፈረሶች ሳይሆን የሐጅ ተግባር የሚፈፀምባቸው ፈረሶችን ነው ብለዋል። በፈረሶች ከመተርጎም ይልቅ በግመል መተርጎም ይመረጣል የሚሉ ብዙ ድጋፍ አላቸው። የተመረጠው የጂሃድ ብሎ መፈሰሩን ነው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَٱلۡعَٰدِيَٰتِ ضَبۡحٗا ١ فَٱلۡمُورِيَٰتِ قَدۡحٗا ٢ فَٱلۡمُغِيرَٰتِ صُبۡحٗا ٣
فَأَثَرۡنَ بِهِۦ نَقۡعٗا ٤ فَوَسَطۡنَ بِهِۦ جَمۡعًا ٥

**1-5.** እያለከለኩ ሩዋጮች በሆኑ (ፈረሶች)፤ ምድርን በሸሆናቸው እያጋጩ እሳትን አውጪዎች በሆኑትም (ፈረሶች)፤ በማለዳ (በጧት) ወራሪዎች በሆኑትም (ፈረሶች)፤ በርሱ አቧራን በቀሰቀሱትና ከዚያም በጠላት ክቢ መካከል እርሱን ይዘው በመግባት በተጋፈጡትም ፈረሶች እምላለሁ።

ከሯጮች ምእራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) በሙንዚር ቢን ዓምር የሚመራው አንድ ቡድን ወደ ኪናና ቢሔር ልከው ስለ ዘገየ እና ወሬአቸው ስለ ጠፋ አስመሳዮች፡- ወደ ዘመቻ የሄዱት ሙስሊሞች ሁሉም አለቁ እኮ ብለው ስለአወሩ ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لِرَبِّهِۦ لَكَنُودٞ ٦ وَإِنَّهُۥ عَلَىٰ ذَٰلِكَ لَشَهِيدٞ ٧ وَإِنَّهُۥ لِحُبِّ ٱلۡخَيۡرِ لَشَدِيدٌ ٨

**6-8.** የሰው ልጅ ለጌታው ብርቱ ከሓዲ ነው። እርሱም (የሰው ልጅ)*1 በዚያ ክህደቱ ላይ መስካሪ ነው። እርሱም ገንዘብን በመውደድ ላይ በጣም ብርቱ ነው።*2

✶1 አላህ ለማለት የሚቻልና የሚመረጠዉም ይህ አባባል ቢሆንም ለሰው ልጅም ማለት ሊሆን እንደሚችል የተፍሲር ምሁራን ይናገራሉ።

✶2 (6) ኛው አንቀፅ በአንዳንድ ሰዎች ተፍሲር የሰው ልጅ ክህደቱን በራሱ ይመሰክራል ማለትን ሲያመለክት «እነዚያ እነሱ ስራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ህይወት ስራቸው የጠፋባቸው ናቸው» (18፡104)

«እርሱም ቅኑን መንገድ የተመራን ነው ብለው ያስባሉ» (17፡ 30)

እና«ለእነርሱም ከአላህ ዘንድ ያስቡት ያልነበሩት ሁሉ ይገለፅላቸዋል» የሚሉት ደግሞ የዚያን ተቃራኒ ይመለከታሉ። ሁለቱን እንዴት ማስማማት እንዳለበት ሲያብራሩ ሁኔታው እንደሚመሰክር ነው ማለት ነው።«የሰው ልጅ በራሱ ላይ የሚመሰክረው (በነፍሶቻችሁ ላይ እርሱ ከሃዲዎ የነበሩ መሆናቸውን መሰከሩ» (16፡ 130) «በየኃጢአታቸውም ያምናሉ ከእሳት ጓዶችም (ከእዝነት) መራቅ የተገባቸው» (67፡ 11) እንዳለው ሁሉ የቂያማ ዕለት መሆኑን ነው።

※ أَفَلَا يَعْلَمُ إِذَا بُعْثِرَ مَا فِي ٱلْقُبُورِ ﴿٩﴾ وَحُصِّلَ مَا فِي ٱلصُّدُورِ ﴿١٠﴾
إِنَّ رَبَّهُم بِهِمْ يَوْمَئِذٍ لَّخَبِيرٌۢ ﴿١١﴾

**9-11.** (የሰው ልጅ) በመቃብሮች ዉስጥ ያሉት ሙታን ሁሉ በተቀሰቀሱ ጊዜ ምን እንደሚከሰት አያውቅምን? በልቦች ውስጥ ያለውም ሁሉ በተገለፀ ጊዜ (እንዴት እንደሚሆን አያውቅምን?) ጌታቸው በዚያ ቀን በእነርሱ ነገር በእርግጥ ውስጠ አዋቂ ነው።

### ከሯጮች ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-11) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. አላህ በፈለገው መማል እንደሚችልና የሰው ልጅ ከአላህ በስተቀር በምንም መማል እንደማይችል፤
2. የሰዉን ልጅ ካሃዲነት የሰው ልጅ እምነት ከሌለው አላህ ለዋለለት ውለታና ለለገሰለት ፀጋ ከሃዲ ስለመሆኑ፤
3. ለትክክለኛ መስፈርቱ ለተሟላ ለጂሀድ ሰዎችን መገፋፋት ለራስም መዘጋጀት እንደሚያስፈለግ፤
4. የሰው ልጅ ካላመነ በስተቀር ገንዘብን በጣም ከሚገባው በላይ እንደሚወድ፤
5. ሙቶ መነሳትና ምንዳ ያለ መሆኑን ማረጋገጥ፤
6. ከሰዎች መደበቅ ቢቻልም ከአላህ መደበቅ እንደማይቻል፤ 7. በዉስጣችን የምናስበዉን ሁሉ አላህ እንደሚያውቀውና አንድ ቀን የሚያወጣበት ቀን እንዳለው እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የሯጮች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (101)
## የቆርቋሪይቱ ምዕራፍ
## (ሱረቱ-አል-ቃሪዐህ)

سُورَةُ القَارِعَةِ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (11) ናቸው።
### የሱረቱ አል ቃሪዓህ መግቢያ

የሰዎችን ፊት የሚለዋውጠውን የገሀነምን ቅጣት ክብደት በማውሳት ይጀምራል። ሰዎችም ሆኑ ጋራዎች በዚ ጊዜ ምን እንደሚሆኑ አውስቷል። ሰዎች የስራቸው ዋጋ ሲሰጣቸው ቀን ምን ምን እንደሚጠብቃቸው በማውሳት መልዕክቱን ያጠቃልላል። በጣም አስደንጋጭ ከመሆኑ የተነሳ አንድ ቀን ዑመር ኢብን ዐብዱል ዐዚዝ ስምተውት አዕምሯቸውን እስከሚስቱ ድረስ ደንግጠው «ወይኔ ሰዎች ተበታትነው እንደቢራቢሮ በሚሆኑበት ቀን፤ ጋራዎችም እንደ ተነደፈ ሱፍ በሚሆኑበት ቀን ምን ይበጀኝ ይሆን እያሉ ሙሉ ሌሊት አነጉ» ይባላል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

ٱلۡقَارِعَةُ ۝١ مَا ٱلۡقَارِعَةُ ۝٢ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡقَارِعَةُ ۝٣

**1-3.** ቆርቋሪይቱ (ጩኸት)፤ ምን አስደናቂ ቆርቋሪ ናት! (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ቆርቋሪይቱ ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?

يَوۡمَ يَكُونُ ٱلنَّاسُ كَٱلۡفَرَاشِ ٱلۡمَبۡثُوثِ ۝٤ وَتَكُونُ ٱلۡجِبَالُ كَٱلۡعِهۡنِ ٱلۡمَنفُوشِ ۝٥

**4-5.** ሰዎች እንደተበታተነ ቢራቢሮ (ኩብኩባ) በሚሆኑበት ቀን፤ ጋራዎችም እንደ ተነደፈ ሱፍ የሚሆኑበት (ቀን ልቦችን በድንጋጤ ትቆረቁራለች)።

فَأَمَّا مَن ثَقُلَتۡ مَوَٰزِينُهُۥ ۝٦ فَهُوَ فِي عِيشَةٖ رَّاضِيَةٖ ۝٧

**6-7.** (ከዚያ በዚያ ዕለት ያ)፣ ሚዛኖቹ የከበዱለት ሰውማ እርሱ ኑሮው በዚያች በምትወደደው (በጀነት) ውስጥ ይሆናል።

وَأَمَّا مَنۡ خَفَّتۡ مَوَٰزِينُهُۥ ۝٨ فَأُمُّهُۥ هَاوِيَةٞ ۝٩ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا هِيَهۡ ۝١٠ نَارٌ حَامِيَةُۢ ۝١١

**8-11.** ሚዛኖቹ የቀለሉበት ሰውማ ደግሞ መኖሪያው ሃዊያህ (የምትባል የጀሃነም ሳት) ናት። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ስለ እርሷ ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ? (እርሷ) በጣም ተኳሳ እሳት ናት።

**ከቆርቋሪይቱ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-11) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ሙቶ መነሳትና የምንዳ ቀንን መኖር ማረጋገጥ፤
2. የቂያማ ቀን ሚዛን እንዳለና መልካም ስራም ሆነ መጥፎ ተግባር ራሱ እንደሚመዘን፤
3. ከቂያማ ዕለት ሰቆቃ ድንጋጤ ማስጠንቀቅ፤
4. ስራዎች እንደሚመዘኑና ምንዳውም በዚሁ መሰረት እንደሚሆን፤
5. ሰዎች በቂያማ ዕለት ሁለት ቡድን እንደሚሆኑና አንዱ የጀነት ሲሆን ሌላኛው የገሀነም እንደሚሆን፤
6. መልካም ስራውና መጥፎ ተግባሩ እኩል የሆነበት ሰው ምን እንደሚሆን በዚህ በ (47) ኛው አንቀፅ ውስጥ ግልፅ ባይሆንም ከእሱረቱል አዕራፍ ላይ በጀነትና በጀሀነም መካከል እንደሚሆኑ ተገልጧል፤
7. ጀሀነም እሳት ብትሆንም ወንጀለኞች ሌላ መጠጊያ ስለላቸው እሷኑ እንደ እናት ያደረገባቸው መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የቆርቋሪይቱ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

ምዕራፍ (102)

# በብዛት የመፎካከር ምዕራፍ

(ሱረቱ አት-ተካሱር)

سُورَةُ التَّكَاثُرِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (8) ናቸው።

## የሱረቱ አት-ተካሱር መግቢያ

ይህ ምዕራፍ በዱንያ ሀብትና በዘር መፎካከር ግዴታቸውን በአግባቡ ከመውጣት የከለከላቸው ሰዎች አውግዞ መጨረሻቸው ምን እንደሚመስል ያስጠነቅቃል። ይህን የሚያደርጉ ሰዎችም ቢያስቡ እሳትን በአይናቸው እንደሚያዩ አስፈራረቶ በዚህች ዓለም ሲኖሩም የተሰጣቸውን ፀጋ አንድ በአንድ እንደሚጠይቁበት ያስፈራራል። የቀብር ዘገባ በግልፅ የተወሳው በቁርኣን በዚህ ምዕራፍብቻ ነው የተዘገበው። ስለ ቀብር በግልፅ ባይሆንም በሌሎቹ ምእራፎች ብዙ አንዖች ሰለፎች ጠቅሰዋል በአል አንዓም (93) በአስ-ሰጅደህ ምዕራፍ -(21) በጋፊር-(46) በአል አንፋል -(50) ያሉት አናቅፅ በብዙ ሰለፍች ዘንድ ስለ ቀብር ነው የተፈሰረው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

أَلۡهَىٰكُمُ ٱلتَّكَاثُرُ ﴿١﴾ حَتَّىٰ زُرۡتُمُ ٱلۡمَقَابِرَ ﴿٢﴾

**1-2.** (ሰዎች ሆይ!) (በዚህች ዓለም ፀጋዎች) በብዛት መፎካከር (ጌታችሁን ከመገዛት)፤ አዘናጋችሁ መቃብሮችን እስከጎበኛችሁ ድረስ፤ (በዚሁ ላይ ቀጠላችሁ)። (እስከምትሞቱ ድረስ ቀጠላችሁ)።

በብዛት የመፎካከር ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከቤታቸው ሲወጡና ሲገቡ ያስቸግራቸው በነበረው በኡበይ ኢብኑ ኸለፍ ምክንያት ነው የወረደው ሲሉ አንዳንዶች ደግሞ በአኽነስ ኢብኑ ሸሪቅ ምክንያት ነው የሚሉም አሉ። (ሱዩጢ)

كَلَّا سَوۡفَ تَعۡلَمُونَ ﴿٣﴾

**3.** (ከዚህ ተግባራችሁ) ተከልከሉ (ታቀቡ)፤ ወደፊት (ውጤቱን) ታውቃላችሁ፤

ثُمَّ كَلَّا سَوۡفَ تَعۡلَمُونَ ﴿٤﴾

**4.** (ከዚያም ከዚህ ተግባራችሁ) ተከልከሉ፤ ወደ ፊትም ታውቃላችሁ፤

كَلَّا لَوۡ تَعۡلَمُونَ عِلۡمَ ٱلۡيَقِينِ ﴿٥﴾

**5.** በእውነቱ (የሚጠብቃችሁን) እርግጠኛ እውቀትን ብታውቁ ኖሮ ይህን ያክል (ባልተዘናጋችሁ ነበር)።

لَتَرَوُنَّ ٱلۡجَحِيمَ ۝٦ ثُمَّ لَتَرَوُنَّهَا عَيۡنَ ٱلۡيَقِينِ ۝٧

**6-7.** ገሀነምን በእርግጥ ታያላችሁ። ከዚያም እርግጠኛን ማየት ታዩዋታላችሁ፤

ثُمَّ لَتُسۡـَٔلُنَّ يَوۡمَئِذٍ عَنِ ٱلنَّعِيمِ ۝٨

**8.** ከዚያም በድሎታችሁ ሁሉ በዚያ ቀን ትጠየቃለችሁ።

**በብዛት ከመፎካከር ምዕራፍ ከ (1-8) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ግዴታውን የማይወጡትለት ገንዘብ አደገኛነት፤
2. ስለ ቀብር ቅጣት መኖር ማረጋገጥ፤
3. ስለ ቀብር ጉብኝት አስፈላጊ መጠቆም፤
4. ሙቶ መነሳትና ከዚያም የስራን ዋጋ ማግኘት ያለ መሆኑን፤
5. አላህ ለሰጠው ውለታ ሁሉ መጠየቁ የማይቀር ሀቅ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ በብዛት የመፎካከር ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (103)
# የጊዜያት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-አስር)

سُورَةُ العَصۡرِ

**በመካ የወረደ ምእራፍ ነው። የአናቅፁ ብዛት ሶስት ናቸው።**
**የሱረቱ አል ዓስር መግቢያ**

ይህ ምዕራፍ ሱረቱ ወል አስር በመባልም ይታወቃል። ዘመን ያጠቃለለው አስገራሚ ክስተትንና ድንቅ ሁኔታዎች የሚያካትት ሲሆን አላህ በፈለገው መማል የሚችል መሆኑን በግልፅ ያሳያል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَٱلۡعَصۡرِ ١ إِنَّ ٱلۡإِنسَٰنَ لَفِي خُسۡرٍ ٢ إِلَّا ٱلَّذِينَ ءَامَنُواْ وَعَمِلُواْ ٱلصَّٰلِحَٰتِ وَتَوَاصَوۡاْ
بِٱلۡحَقِّ وَتَوَاصَوۡاْ بِٱلصَّبۡرِ ٣

**1-3.** በጊዜ እምላለሁ፤ ሰው ሁሉ በእርግጥ በኪሳራ ውስጥ ነው። እነዚያ በአላህ በትክክል ያመኑትና መልካሞችን የሰሩ፤ በእውነትም አደራ የተባባሉ፤* በመታገስም አደራ የተባባሉ ብቻ ሲቀሩ።

* እውነት የሚለው ቃል ቁርኣን፤ ኸይር ነገር ሁሉ ማለት ነው ተብሏል።

በእውነት ነገር ላይ አደራ መባባል የነብያት መንገድና አደራቸውም ነው። አላህ፡- «ለእናንተ ከሃይማኖት ያንን በርሱ ኑህን....» (42፡ 13) ብሏል።

በዲን ላይ አደራ መባባል የነብያት ፈለግ ነው። አላህ እንዲህም አለ «በእርሷም (በህግጋቲቱ) ኢብራም ልጆቹን....» (2፡ 132)

ትዕግስት ለሁሉም ነገር አስፈላጊ ነው። በተለይም ለመልካም ሰሪዎች በይበልጥ ሰዎችን ለማስተማር ለሚያስቡ ሁሉ ለስራቸው መቃናት ከሁሉ የበለጠ አስፈላጊው ነገር ትዕግስት ነው። ሉቅማን ለልጃቸው ከለገሰሱለት ምክር መካከል የሚከተለው አባባል ነበረበት «ልጄ ሆይ! ሶላትን አስተካለህ ስገድ በበጎ ነገርም... በሚያገኘህ መከራ ላይ ታገስ .» (31፡ 17)

ይህ ምዕራፉ የሚያስተምራቸውን አራት ዋና ዋና ነገሮችን መፈፀም ግድ ነው።

1.ኛ. እውቀት ሲሆን፡- እሱም አላህን፤ መልዕክተኛዉንና ኢስላምን ማወቅ ነው። ምክንያቱም አላህን ያለውቀት መገዛት ፋይዳ የለውም። ይህን ያደረገ ሰው የጠመመ ሲሆን በዚህም ተግባር ስህተት ላይ ይወድቃል።

2.ኛ. ተግባር ሲሆን፡- አውቆ በእውቀቱ ያልሰራበት ሁሉ በእውቀታቸው ያልሰሩትን አይሁዶች ይመስላል። ከሰይጣን ዘዴዎች አንዱ ሰዎችን ካወቁ እንደሚጠየቁና ካላወቁ ግን ከዚህ ችግር ነፃ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማስመሰል ከትምህርት መድረክ ማሸሽ ነው።

3. ኛ. ወደ ዚሁ ዲን ጥሪ ማድረግ ሲሆን፡- አዋቂዎችና ዳዒዎች የነቢያት ወራሾች ናቸው። አላህ የኢስራኢል ልጆችን (ይሰሩት ከነበረው መጥፎ ተግባር አይከላከሉም ነበር) እንዳላቸው ስለ ነበሩ እረገማቸው። ደዕዋ ማድረግና ማስተማር ሁሉም ከተወው ሁሉንም ወንጀለኛ የሚያደርግ እናም በከፊል ህብረተሰብ እንኳን ቢሆን ሊሸፈን ግዴታ የሆነ ጉዳይ ነው።

4.ኛ. በማስተማር፤ በመተግበርና ወደ እሱ ጥሪ በማድረግ ሂደት ላይ የሚያጋጥሙ አያሌ መሰናክሎችን ለማለፍ ትዕግስት ማድረግ ነው።

**ከጊዜያት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-3) ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ከሃዲ መጨረሻው ዘለአለማዊ ክስረት መሆኑን፤
2. በአላህ ያመኑና መልካም የሰሩ ሰዎች ክብርና ግዴታ መሆኑን፤
3. በእውነትና በትዕግስት ለሀቅ መዋገታና መከራር ግዴታ መሆኑን፤
4. ሰዎችን ለማስተማር የሚንቀሳቀስ ሁሉ እውነቱን ሊደብቃቸው እንደማይገባ፤
5. ሰዎችን ለማስተማር የሚንቀሳቀስ ሰው ብዙ ችግር ሊያጋጥመው እንደሚችል ከወዲሁ የመንፈስ ዝግጅት አድርጎ ሊጠበቃቸው እንደሚገባ፤
6. ሀቅን የሚፈልግ ሰው ሁሉ እስኪገኝለት ድረስ በትዕግስት መጠበቅ እንደሚገባ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የጊዜ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (104)
# የሀሜተኛ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ሁመዛህ)

سُورَةُ الهُمَزَةِ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (9) ናቸው።**
**የሱረቱ አል ሁመዛህ መግቢያ**

ይህ ምዕራፍ ወይ ሊሊኩሊ ሁመዛህ ምዕራፍ እና አልሁጠመህ ምዕራፍ በመባልም ይታወቃል። ሰዎችን በይፋም ሆነ በአሽሙር ማንቋሸሽና ማነወር ሊያስከትል ከሚችለው አደጋ ያስጠነቅቃል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

وَيۡلٞ لِّكُلِّ هُمَزَةٖ لُّمَزَةٍ ١ ٱلَّذِي جَمَعَ مَالٗا وَعَدَّدَهُۥ ٢ يَحۡسَبُ أَنَّ مَالَهُۥٓ أَخۡلَدَهُۥ ٣

**1-3.** ለሐሜተኛ፤ ዘላፊ፤ (ለአሽሟጣጭ) ሁሉ ወዮለት። ለዚያ ገንዘብን የሰበሰበና የቆጣጠረው (ያደለበውም) ለሆነ ሁሉ (ወዮለት)። ገንዘቡ (በዚህች ዓለም) የሚያዘወትረው መሆኑን ያስባል።

كَلَّاۖ لَيُنۢبَذَنَّ فِي ٱلۡحُطَمَةِ ٤ وَمَآ أَدۡرَىٰكَ مَا ٱلۡحُطَمَةُ ٥

**4-5.** (ከዚህ ነገር) ይከልከል፤ በሰባሪይቱና አውዳሚቱ እሳት ውስጥ በእርግጥ ይጣላል። (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ሰባሪይቱም ምን እንደሆነች ምን አሳወቀህ?

نَارُ ٱللَّهِ ٱلۡمُوقَدَةُ ٦ ٱلَّتِي تَطَّلِعُ عَلَى ٱلۡأَفۡـِٔدَةِ ٧ إِنَّهَا عَلَيۡهِم مُّؤۡصَدَةٞ ٨ فِي عَمَدٖ مُّمَدَّدَةِۭ ٩

**6-9.** ያቺ የተነደደችው የአላህ እሳት ናት። ያቺ በልቦች ላይ እንኳን ሳይቀር የምትዘልቅ የሆነች። እርሷ በእርግጥ በእነርሱ ላይ በተዘረጋች አዕማድ ውስጥ የተዘጋች ናት።

**ከሀሜተኛ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-9) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ**

1. ሙቶ መነሳትና በሰሩት ምንዳ ማግኜት አይቀሬ መሆኑን፤
2. ሀሜትንና ነገር ማዋሰድን ማውገዝ፤
3. በንብረት የሚመኩ ሁሉ ጠንካራ ቅጣት እንደሚጠብቃቸው፤
4. የገሀነም እሳት ምን ያህል ብርቱ መሆኑንና የገባባትን ሁሉ እንደምታምም እንማራለን።

**በአላህ ፈቃድ የሀሜተኛ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።**

# ምዕራፍ (105)
# የዝሆኑ ምዕራፍ
# (ሱረቱ አል-ፊል)

سُورَةُ الفِيلِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (5) ናቸው።

## የሱረቱ አል ፊል መግቢያ

ይህ ምእራፍ አለምተረ በመባልም ይታወቃል። የተከበረውን ቤት ከዕባን ለማፍረስ ከየመን ተነስቶ ወደ መካ ተዘጋጅቶ ሂዶ የነበረው ሐበሻዊ ወራሪ ቡድን የደረሰበትን ታሪክና አስተምህሮት ነብዩ እንዲያስታውሱ አስተምሮ አላህ በየጊዜው የሱን ህግጋትና ደንብ በሚያልፍ ሰዎች ሁሉ ላይ ተመሳሳይ እርምጃዎች እንደሚወሰድባቸው ያስተምራል። ይህ ታሪክ የተከሰተው ነብዩ በተወለዱበት አመት እንደነበር እራሳቸው የተወለድኩት በዝሆኑ አመት ላይ ነው ብለው አስተምረዋል። ሌላው ነብዩ (ﷺ) ሲላኩ ይህን ታሪክ በትክክል ያውቁ የነበሩ ሰዎች ነበሩ።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

أَلَمۡ تَرَ كَيۡفَ فَعَلَ رَبُّكَ بِأَصۡحَٰبِ ٱلۡفِيلِ ١ أَلَمۡ يَجۡعَلۡ كَيۡدَهُمۡ فِي تَضۡلِيلٖ ٢ وَأَرۡسَلَ عَلَيۡهِمۡ طَيۡرًا أَبَابِيلَ ٣ تَرۡمِيهِم بِحِجَارَةٖ مِّن سِجِّيلٖ ٤ فَجَعَلَهُمۡ كَعَصۡفٖ مَّأۡكُولِۭ ٥

**1-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ጌታህ አላህ በዝሆኑ ባለቤቶች ላይ እንዴት እንደሰራ አላወቅክምን? ተንኮላቸውን በጥፋት ውስጥ ከንቱ አላደረገምን? (አድርጓል) በእነርሱ ላይ ከተጠበሰ ጭቃ የሆነን ጠጠር የምትወረውርባቸውን የአዕዋፍ መንጎችን ላከባቸው። እና ቅጠሉ እንደ ተበላ አዝመራ አደረጋቸው።✳

✳ ከዝሆኑ ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፦ ከዕባን ሊያፈርሱ ወደ መካ ተጉዘው የነበሩትን ሐበሻዊያን ሀይል እንዴት እንደመለሳቸውና ካዕባን ቀደም ሲልም እንዴት እንደ ተንከባከበው የሚያሳየውን ታሪክ ለመካ ሰወች ለማስታወስ ነው። (ዋሒዲ)

የዝሆን ጦርነትን አስመልክቶ በዚህ ምዕራፍ ላይ የተጠቀሰው ታሪክ የተከሰተው ነብዩ (ﷺ) በተወለዱበት ዓመት ላይ ነበር። በየመን ሀገር የነበረው የሐበሻው ንጉስ ወኪል አብረሃ ሰንዐእ ከተማ ውስጥ ሰዎች የሚጎበኙት ልክ አንድ ካዕባ የመሰለ ሕንፃ ለመገንባት ፈለገ በዚህ መሰረት ዐረቦች ወደ ከዕባ የሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉብኝት ወደ ሰንዐህ የየመን ዋና ከተማ እንዲዞር ፅኑ ፍላጎት ነበረው። ስለሆነም ያለውን ሀሳብ ለሀበሻው ንጉስ አቀረበ። ንጉሱም አብረሃ ባቀረበው ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ተስማማ። በስምምነቱ መሰረትም «አል ቁለይስ» የተባለ ቤተ. ክርስቲያን ሰራ። በወቅቱም ይህን የመሰለ ቤተክርስቲያን ተሰርቶ አያውቅም ነበር። አንድ ከመካ የመጣ ሰው ወደዚህ ቤተ ክርስቲያን በመምጣት ቤተ ክርስቲያኑን በሰገራና በሽንት አቆሸሸው።

አብርሃም ይህን በተመለከተ ጊዜ ንዴቱን መቆጣጠር አልቻለም። ስለዚህ ግዙፍ ጦር አዘጋጅቶ መካ ለመውረርና ከዕባን ለማጥፋት ወሰነ። ባዘጋጀው ጦር ውስጥ አስራ ሶስት ዝሆኖች የሚገኙ ሲሆን በመካከላቸውም ከምድረ ገፅ ማሕሙድ የሚባል የቤተ መንግስት ቅልብ ዝሆን ይገኝበታል። ይህ ዝሆን ከሁሉም ዝሆኖች የበለጠ ግዙፉ ነበር። በወቅቱ ማንም የዐረብ ጎሳ ከአብረሃ ጦር ጋር የተጋፈጠና የተዋጋ የለም። በዚህም መሰረት ያገኘውን ሁሉ እያሸነፈና እየገደለ ወደ መካ ከተማ በጣም ተቃረበ። በዚህም ወቅት በነብዩ አያት በዐብዱል ሙጠሊብና በአብረሃ መካከል የእርቀ ሰላም ስምምነት ቢደረግም አብረሃ ለእርቀ ሰላም ማስፈፀሚያ ከዐብዱ ሙጠሊብ የወሰደውን ግመሎች በመመለስ መካ ገብቶ ካዕባን በማጥፋቱ ላይ ፀና። ዐብዱል ሙጠሊብም መካ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ሊከሰት ከሚችለው ከሰማይ መቅሰፍት ይጠበቁ ዘንድ ከተማዋን ለቀው ከሚስቶቻቸውና ከልጆቻቸው ጋር ከፍ ወዳለ ስፍራ እንዲወጡ ነገሯቸው። ሰዎቹም ወደ ከፍታ ስፍራው ሄዱ። የአብረሃም ጦር መካ ከተማ መግቢያ ላይ አል. ሙሐሲር የሚባለውን ሸለቆ ድረስ ጉዞውን ቀጠለ። በሸለቆው መሐል ሲደርሱ በወፎች ተከበቡ። አእዋፋቱ በእግሮቻቸው የበቀልት መጠን ያላቸውን ጠጠሮች ይዘው የእያንዳንዱን ወታደር ስጋ በትንንሹ እስኪቆራረጥ ድረስ ጠጠሩን ወረወሩ። ከፍተኛ ጥቃትና ጥፋትም አደረሱ። አብርሃት ከዚህ ጥቃት ለመሸሽ ወደ የመን አቀና። ነገር ግን መንገድ ላይ እያለ ስጋው ተበጣጠሰ። ይህ እንግዲህ አላህ በጠላቶቹ ላይ የተቀዳጀው ድል ከመሆኑም ባሻገር አላህ ካዕባንና መካ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎችን የጠበቀበት ክስተት ነው» በአጥ- ጦበሪ የቁርኣን ትንታኔ መፅሐፍ ውስጥ ተዘግቧል።

**ከዝሆኑ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የታሪክን አስተማሪነት በሰፊው መዘገብ፤
2. አንድን ታሪክ በተለይ በሰዎች ዘንድ የታወቀ ከሆነ በአጭሩ መጥቀስ እንሚቻል፤
3. ነብዩ (ﷺ) የቁረይሽ ከሓዲያን በሚያደርሱባቸ ችግርና ስቃይ እንዳይበሳጩ ማፅናናት አላህ ካዕባ እንደጠበቀ ሁሉ ነብዩንም (ﷺ) ሆነ ኢስላምን ከፈለገው ኃይል እንደሚጠብቃቸው፤
4. ሙስሊሞች ላይ ስቃይ ሲፈፅሙ ቁረይሾች የአላህን ኃይልና ቅጣት እንዲስታውሱ ማድረግና መጋበዝ፤
5. አላህ ጠቅላላ ኃይሉን ማሳየትና ማሳወቅ፤
6. በምድር ሳለ በጉልበት፤ በሀብትና በስልጣን የሚደነፋ ሁሉ በአላህ ዘንድ ቅንጣት ያህል እንደማይከብድ እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የዝሆኑ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (106)
# የቁረይሾች ምዕራፍ
## (ሱረቱ ቁረይሽ)

سُورَةُ قُرَيْشٍ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (4) ናቸው።
### የሱረቱ አል ቁረይሽ መግቢያ

ይህ ምዕራፍ ከዝሆኑ ምዕራፍ ጋር የጠበቀ ቁርኚት አለው። የዝሆኑ ዋና ጠላታቸውን አሳፍሮ በመመለስ በዋለላቸው ዉለታ ላይ ያተኮረ የቁረይሽ ደግሞ በአንድ ሁነው የበጋዉንም ሆነ የክረምቱን ንግድ በአንድ እንዲያካሂዱ በማድረጉ ላይ ያተኩራል። ከዚህ በመነሳት ይመስላል ኡበይ ብን ከዕብ አንድ ምዕራፍ ናቸው ይሉ የነበሩት። ሆኖም በይዘት ይቀራረቡ እንጂ በመሐከላቸው ዘጠኝ ምእራፎች እንዳሉ የተፍሲር ምሁራን ይገልፃሉ።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

لِإِيلَٰفِ قُرَيۡشٍ ١ إِۦلَٰفِهِمۡ رِحۡلَةَ ٱلشِّتَآءِ وَٱلصَّيۡفِ ٢ فَلۡيَعۡبُدُواْ رَبَّ هَٰذَا ٱلۡبَيۡتِ ٣
ٱلَّذِيٓ أَطۡعَمَهُم مِّن جُوعٖ وَءَامَنَهُم مِّنۡ خَوۡفِۭ ٤

**1-4.** አላህ ቁረይሽን ለማላመድ (ባለ ዝሆኖቹን አጠፋ)። የክረምትንና የበጋን ወራት ጉዞዎች ሊያላምዳቸው (ይህንን ሰራ)፤ ስለዚህ የዚህን ቤት (የካዕባን) ጌታ ብቻ ይገዙ። ያንን ከርኃብ ያበላቸውን፤ ከፍርሃትም ያዳናቸውን (ጌታ ብቻ ያምልኩ)።

**ከቁረይሾች ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-4) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. ለመካ ሰዎች ህይወት መስተካከል ንግድ የሚኖረው ከፍተኛ ሚና፤
2. የአላህን ፀጋዎች በምስጋና መቀበል ግዴታ መሆኑን፤
3. ጥበበኛና ሩህሩህ የሆነው ጌታ የአላህ ቅንብር ምን ምን እንደሚመስል፤
4. አላህ ለቁረይሾች የዋለው ታላላቅ ፀጋና እሱን ባለማመስገናቸው ያጋጥማቸው ችግር ምን እንደሆነ፤
5. አላህን በብቸኝነት ማምለክ ግዴታ ስለ መሆኑ፤
6. የአላህን ፀጋዎችን ማመስገን ግዴታ ስለ መሆኑ፤
7. በቂ ምግብና የተሟላ ሰላም ማስገኘት ያለ አላህ ማንም ሊያደርገው እንደማይቻል፤
8. ቁረይሽ ሌላው ቀርቶ ለተዋለላቸው ፀጋ እንኳን ሲሉ የአላህን ብቸና አምላክነት መቀበል እንደነበረባቸው እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የቁረይሾች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (107)
## የእቃ መዋዋስ ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ማዑን)

سُورَةُ المَاعُونِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (7) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

أَرَءَيۡتَ ٱلَّذِي يُكَذِّبُ بِٱلدِّينِ ١ فَذَٰلِكَ ٱلَّذِي يَدُعُّ ٱلۡيَتِيمَ ٢
وَلَا يَحُضُّ عَلَىٰ طَعَامِ ٱلۡمِسۡكِينِ ٣ فَوَيۡلٞ لِّلۡمُصَلِّينَ ٤
ٱلَّذِينَ هُمۡ عَن صَلَاتِهِمۡ سَاهُونَ ٥ ٱلَّذِينَ هُمۡ يُرَآءُونَ ٦
وَيَمۡنَعُونَ ٱلۡمَاعُونَ ٧

**1-7.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) ያንን በምርመራው ቀን የሚያስተባብለውን ሰው (አወቅከውን?) ይህም ያ የቲምን*1 በኃይል የሚገፈትረው፤ ድሆንም በማብላት*2 ላይ የማያግባባው (የማያነሳሳ) ሰው ነው። ወዩውላቸው ለሰጋጆች፤ ለእነዚያ እነርሱ ከስግደታቸው ዘንጊዎች ለሆኑት (ሰጋጆች)፤ ለእነዚያ እነርሱ ይዩልኝ ባዩች ለሆኑት፤ የዕቃ ትውስትንም ሰዎችን የሚከለክሉ ለሆኑት ሁሉ (ወዮላቸው)።

*1 ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሰህል ኢብኑ ሰዕድ እንዳስተላለፉት እንዲህ ብለዋል፡- «እኔና አባቱ የሞተበትን ልጅን የሚንከባከብ ሰው ጀነት ውስጥ እንዲህ ነን»ካሉ በኋላ አመልካችና የቀለበት ጣቶቻቸውን በማሳየት አመለከቱ»

*2 ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት ብለዋል፡- «ባሏ የሞተባትን ወይም ደሃ የሆነን የሚንከባከብ ሰው ልክ በአላህ መንገድ ላይ ትግል እንደሚያደርግ ሰው ወይም ለሊቱን ሙሉ እንደሚሰግድና ቀኑን ሙሉ እንደሚፆም ሰው ነው»

ከዕቃ መዋዋስ ምዕራፍ (3) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- አቡሱፍያን ቢን ሐርብ በየሳምንቱ ሁለት ግመሎች እያረደ ያበላ ነበርና ከዕለታት አንድ ቀን አንድ የቲም መጥቶ ሲለምነው በቁጣ ስለ ገለመጠው እና በዱላ ስላባረረው ነው።

**ከዕቃ መዋዋስ ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-7) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. በመጨረሻው አለም ማስተባበል ክህደት ስለመሆኑ፤
2. የቲምን መጨቆን ታላቅ ወንጀል ስለመሆኑ፤
3. ሶላትን አለመስገድም ሆነ ከሰአቱ በጣም አቆይቶ መስገድ ለቅጣት እንደሚዳርግ፤
4. ለእዩልኝ መስራት መጥፎ ተግባር ስለመሆኑ፤
5. እቃን መዋስ የሚልግን ሰው መከልከል መጥፎ ባህሪ መሆኑን እንረዳለን።

## በአላህ ፈቃድ የዕቃ መዋዋስ ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (108)
## የበጎ ነገሮች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ከውሰር)

سُورَةُ الْكَوْثَرِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (3) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)

إِنَّآ أَعۡطَيۡنَٰكَ ٱلۡكَوۡثَرَ ١ فَصَلِّ لِرَبِّكَ وَٱنۡحَرۡ ٢ إِنَّ شَانِئَكَ هُوَ ٱلۡأَبۡتَرُ ٣

**1-3.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)✶1 እኛ በጣም ብዙ✶2 በጎ ነገሮችን ሰጠንህ (ለገስንህ)። ስለዚህ ለጌታህ በፍፁምነት ስገድ። በስሙም ብቻ ሰዋም። የሚጠላህ ሁሉ እርሱ በእርግጥ ዘሩ የተቆረጠ ነው።

✶1 ምዕራፉ የወረደበት ምክኒያት ዐብዱላህ የተባለው የነቢዩ ልጅ በሞተ ጊዜ አንድ ዓስ ኢብኑ ዋኢል የተባለ ከሃዲ የሙሐመድ ዘር ተቆርጧል እሱ እኮ ዘር የሌለው ሲሞት አስተምህሮቱ የሚገታ ነው) በማለቱ ነው ይህ ዕራፍ የወረደው።

✶2 ከውሰር ብዙ ነገሮችን ለማለት ነው የሚሉ ምሁራን እንዳሉ ሁሉ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አነስ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) ወደ ሰማይ አርገው ከተመለሱ በኋላ እንዲህ ብለዋል፡- «ጀነት ውስጥ ወደ አንድ ዳርቻዎቹ በሉል ወደ ተጌጡ ወንዝ መጣሁና ጅብሪልን ይህ ምንድ ነው? አልኩት። እሱም ይህ ከውሰር ነው አለኝ» ያሉት የጀነት ዉሃ (ሀውድ) ነው የሚሉም ምሁራን አሉ። የሚመረጠው ግን ብዙ የሚለው ነው። ምክንያቱም ዉሃዉም በዚሁ ዉስጥ ስለሚካተት።

### ከምዕራፉ ከምናኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-

1. አላህ ለመልዕክተኛው ሙሐመድ (ﷺ) የሰጠው ማዕረግና ክብር፤
2. በአምልኮ በተለይም በሰላትና በእርድ ዙሪያ ለአላህ ሊኖረው የሚገባ ፍፁምነት፤
3. በግፈኞች ላይ ዱዓ ማድረግ ተገቢ መሆኑን፤
4. ነብዩን (ﷺ) መጥላት ለከፋ ችግር እንደሚያጋልጥ ሁሉ እሳቸውን መውደድም ለመልካም እድል እንደሚያበቃ፤
5. ዱዓቶችን የሚጠሉና በመጥፎ የሚያስቡ ሁሉ መጨረሻቸው እንደማያምር፤
6. ነብዩን (ﷺ) የጠላ ሁሉ ቆራጣ መሆኑን እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የበጎ ነገሮች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (109)
# የከሓዲያን ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ካፊሩን)

سُورَةُ الكَافِرُونَ

### የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (6) ናቸው።
### የሱረቱ አል ካፊሩን መግቢያ

ይህ ምዕራፍ

1. አስሳፊራህ ምዕራፍ፤
2. የኢኽላስ ምዕራፍ፤
3. የዒባዳ ምዕራፍና
4. የዲን ምዕራፍ ይባላል።

ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራህ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ በፈጅር ሁለት ረከዓዎች ውስጥ «ቁል ያ አዩሃል ካፍሩን» እና «ቁል ሁወልላሁ አሐድ» የተሰኙ ምእራፎችን አንብበዋል) ብለዋል።

አላህ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ካፊሮች ነብዩ (ﷺ) ጋር ያደርጉት የነበረውን እውነታዊ ድርድር ተስፋ እንዲቆርጡና መቼውንም ቢሆን ወደ እነሱ እምነት እንደማይገቡ ለአንድ አፍታም ቢሆን ከእሱ ጋር እንደማስማሙ በግልፅ ያውጃል። ይህ አባባል ለእነዚያ (እነዚያ የጌታህ ቃል የተረጋገጠባቸው ተዐምራት ሁሉ ብታመጠላቸውም አሳማሚ ቅጣት እስከሚያዩ ድረስ አያምኑም። የተባሉትንና ለተወሰኑት የከሀዲ ቡድኖች ካልሆነ ወይም ማገኛውም ከሃዲ ከመስለሙ በፊት ተብሎ መፈታት ነው ያለበት።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

قُلۡ يَٰٓأَيُّهَا ٱلۡكَٰفِرُونَ ١ لَآ أَعۡبُدُ مَا تَعۡبُدُونَ ٢ وَلَآ أَنتُمۡ عَٰبِدُونَ مَآ أَعۡبُدُ ٣
وَلَآ أَنَا۠ عَابِدٞ مَّا عَبَدتُّمۡ ٤ وَلَآ أَنتُمۡ عَٰبِدُونَ مَآ أَعۡبُدُ ٥ لَكُمۡ دِينُكُمۡ وَلِيَ دِينِ ٦

**1-6.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) (ለካሓዲያን)፡- እናንተ ከሓዲያን ሆይ፣ ያንን የምትገዙትን (ጣዖት አሁን) አልገዛም። እናንተም እኔ የምገዛውን (አምላክ አሁን) ተገዢዎች አይደላችሁም። እኔም ያንን የተገዛችሁትን (ወደ ፊት) ተገዢ አይደለሁም። እናንተም እኔ የምገዛውን (ወደ ፊት) ተገዢዎች አይደላችሁም። ለእናንተ የራሳችሁ ሃይማኖት አላችሁ። ለእኔም የራሴ ሃይማኖት አለኝ በላቸው።

ከከሓዲያን ምዕራፍ (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- የተወሰኑ አልአስወድ ብኑ አብዱል ሙጠሊብ፤ ወሊድ ኢብኑ ሙጊራህ፤ ኡመየት ኢብኑ ኸለፍ አልዓሲ ከነብዩ (ﷺ) ጋር በጠዋፍ ላይ ተገናኝተው ገንዘብ ከፈለክ የፈለከውን ያህል እንስጥህ ሴት ከፈለክ የፈላካት ምረጥና እንዳርልህ ስልጣን ከፈለክ እናንግስህ ብቻ አምላካችንን ተውልን እንስማማ በዚህ ካልተስማማህ ደግሞ አንድ ዓመት ያንተን ጌታ በሌላው ዓመት ደግሞ የእኛን ጌታ አብረን እንገዛ በማለት ለድርድር ሲቀርቡ ነብዩ (ﷺ) ጌታዬ የሚለኝን እጠብቃለሁ በማለታቸው ነው። (ጦበሪ፤ ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከከሓዲያን ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-6) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. እምነት ማለት፡- በጣኦት ያለመነ፤ ከሃዲ ማለት በጣኦት አምኖ በአላህ የካደ መሆኑን፤
2. አላህ ነብዩ (ﷺ) የከሓዲያንን አስተሳሰብ እንዳቀበሉ የወሰደው ኃላፊነት፤
3. በኩፍር ሰዎችና በእምነት ሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባው በእምነት ጉዳይ ላይ ለምንም ተብሎ መደራደር እንደማይቻል፤
4. በእውነቱ ላይ መድረስ ካልተቻለ ሁሉም የየራሱን ይዞ ለጊዜው መቀጠል ለአፍታም ቢሆን ከኩፍር ጋር መደራደር እንደማይቻል እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የከሓዲያን ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

# ምዕራፍ (110)
# የእርዳታው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አን-ነስር)

سُورَةُ النَّصْرِ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ ብዛት (3) ናቸው።**
**የሱረቱ አን-ነስር መግቢያ**

የመሰናበቻ ምዕራፍ ይባላል የእርዳታው ምዕራፍ ከንሰሃ ምዕራፍ በኋላ በ (114) ኛ ተራ ቁጥር ላይና በምዕራፍደረጃ በመጨረሻ ሁኖ በመዲና የወረደ ምዕራፍ ነው። ይህ ምዕራፍ «ኢዛጃ አነስሩላህ» ምዕራፍ «አል-ፈትህ» ምዕራፍ «አት-ተውዲዕ» በመባልም ይሰየማል።

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አላህ እድል ሲመጣና ሰዎች ወደ ኢስላም በቡድን በቡድን እየሆኑ ሲገቡ ካዩ አላህን ከማጥራት ጋር እንዲያመሰግኑትና ለራሳቸውም ሆነ ምእመናን ከአላህ ምህረት እንዲለምኑ ያስተምራል።

ብዙ የዐረብ ህዝቦች ኢስላምን ለመቀበል የመካን በድል መከፈት በጉጉት ይጠባበቁ ነበር። በህዝቦቹ ላይ ድልን ከተቀዳጀ እውነተኛ የአላህ ነብይ ነው ይሉም ነበር።

አላህ ሙስሊሞችን ለድል አብቅቷቸው መካን ሲከፍቱ ሰዎች በነቂስ ኢስላምን ተቀብሎ። እናም ሁለት አመታት ባልሞላ ጊዜ ዐረቢያ በኢስላም ስር አደረ። ይህ ምዕራፍ ከወረደ በኋላ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) በሩኩዓቸውም ሆነ በሱጁዳቸው ላይ «ሱብሀነከላሁመ ረበና ወቢሀምዲከ አላሁመ ግፊርሊ» የሚለዉን ዱዓ በብዛት ይሉ ነበር። ብለዋል።

ነብዩ (ﷺ) አህመድና ኢብኑ ጀሪር በዘገቡት ሐዲስ «ይህ ምዕራፍ በወረደበት ጊዜ ሞቴ ደረሰ ማለት ነው ብለዋል»።

بِسْمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحْمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

إِذَا جَآءَ نَصْرُ ٱللَّهِ وَٱلْفَتْحُ ﴿١﴾ وَرَأَيْتَ ٱلنَّاسَ يَدْخُلُونَ فِى دِينِ ٱللَّهِ أَفْوَاجًا ﴿٢﴾
فَسَبِّحْ بِحَمْدِ رَبِّكَ وَٱسْتَغْفِرْهُ ۚ إِنَّهُۥ كَانَ تَوَّابًۢا ﴿٣﴾

**1-3.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) የአላህን እርዳታና (የመካ) መክፈት በመጣ ጊዜ፣ ሰዎችም ጭፍሮች ጭፍሮች እየሆኑ ወደ አላህ ሃይማኖት ውስጥ ሲገቡ ባየህ ጊዜ፤ ጌታህን ከማመስገን ጋር አጥራው።* ምህረትንም ለምነው፤ እርሱ ፀፀትን በጣም ተቀባይ ነውና።

* ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «በምላስ ላይ ቀላል፤ በሚዛን ላይ ከባድ፤ አዛኙ አምላክ ዘንድ ደግሞ ተወዳጅ የሆኑ ሁለት ቃላት አሉ። እነሱም «ሰብሐነአላህ ወቢሐምዲሂ ሰብሐነልላሂል ዐዚይም» የሚሉት ናቸው። ብለዋል።

ከእርዳታው (1) ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት፡- ነብዩ (ﷺ) ከሁነይ ዘመቻ ሲመለሱ ነው። (ዋሒዲ እና ሱዩጢ)

**ከእርዳታው ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-3) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. የአላህን ፀጋ ባገኘን ቁጥር ልናመሰግነው ልናጠራው እንደሚገባ፤
2. ድል ከአላህ እንጂ በጉልበትም ሆነ በሀብት እንዳልሆነ፤
3. ኢስላም በውድ እንጂ የተስፋፋው በግድና በኃይል አለመሆኑን፤
4. የሰው ልጅ የቱንም ያህል ወንጀለኛ ቢሆን ከአላህ ምህረትን መጠየቅ እንደሚገባ፤
5. በሙስሊሙ ዘንድ መሪ የሆነ ሰው ተከታዩን በየጊዜው መገምገም፤
6. የዚህ ዲን ድል ቀጣይነት ያለውና ዓለምን እንደሚያጥለቀልቀው፤
7. የነብዩ (ﷺ) እድሜ ማለቁን ማመልከቷን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የእርዳታው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (111)
## የጭረት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-መሰድ)

سُورَةُ المَسَدِ

### የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (5) ናቸው።
### የሱረቱ አል መሰድ መግቢያ

ምዕራፉ የአቡ ለሀብን መጥፋትና ንብረትም ሆነ ዝናው እንዲሁም ወገኑ ከአላህ ቅጣት የማያድነው መሆኑን አብስሮ በመጥፎ ስራ ተባብራ የነበረችው ባለቤቱ የመጨረሻ እጣ ፈንታዋ ገሀነም እሳት ውስጥ መማገድ መሆኑን ያበስራል።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

تَبَّتۡ يَدَآ أَبِي لَهَبٖ وَتَبَّ ١ مَآ أَغۡنَىٰ عَنۡهُ مَالُهُۥ وَمَا كَسَبَ ٢ سَيَصۡلَىٰ نَارٗا ذَاتَ
لَهَبٖ ٣ وَٱمۡرَأَتُهُۥ حَمَّالَةَ ٱلۡحَطَبِ ٤ فِي جِيدِهَا حَبۡلٞ مِّن مَّسَدِۭ ٥

**1-5.** የአቡ ለሀብ ሁለት እጆች ከሰሩ፤ (ጠፉ)። እርሱም ከሰረ፤ (ጠፋ)። ከእርሱ ገንዘቡና ያም ያፈራው ሁሉ ምንም አልጠቀመውም። የመንቀልቀል ባለቤት የሆነችን እሳት በእርግጥ ይገባል። ሚስቱም ትገባለች፣ እንጨት ተሸካሚ ስትሆን፤ በአንገቷ ላይ የጭረት ገመድ* ያለባት ስትሆን (ትገባለች)።

**ከመንቀልቀል ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አቡ ለሀብ በማጥፋትና ተንኮሉን መና በማስቀረት የአላህን የበላይነት ማረጋጥ፤
2. የሰው ልጅ ገንዘብም ሆነ ልጁ ከአላህ ቁጣ ቅንጣት ያህል እንደማያድኑት፤
3. አማኒያንን ማንገላታ ክልክል መሆኑን፤
4. በኢስላም በዘርም ሆነ በወገን መዳን አለመቻሉን አቡለሀብ የነብዩ (ﷺ) አጎት እሳት መግባቱ በግልፅ እንደሚያሳይ፤
5. ቁርአን የአላህ ቃል መሆኑንና የትንቢቱን ተዐሚነት በግልፅ ማየት፤
6. ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የአቡ ለሀብንና የባለቤቱን አለመስለም በግልፅ መናገራቸው ነብይነታቸውን እንደሚያመለክት እንማራለን።

በአላህ ፈቃድ የመንቀልቀል ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (112)
## የፍፁምነት ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ኢኽላስ)

سُورَةُ الإِخۡلَاصِ

**የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ ብዛት (4) ናቸው።**

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

قُلۡ هُوَ ٱللَّهُ أَحَدٌ ١ ٱللَّهُ ٱلصَّمَدُ ٢ لَمۡ يَلِدۡ وَلَمۡ يُولَدۡ ٣ وَلَمۡ يَكُن لَّهُۥ كُفُوًا أَحَدُۢ ٤

**1-4.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!)[*1] እርሱ አላህ አንድ ብቻ ነው። አላህ (የሁሉ) መጠጊያ ነው። አልወለደም፤ አልተወለደምም። ለእርሱ አንድም (አምሳያ) የለውም በል[*2]።

*1 ይህ ምዕራፉ የወረደበትን ምክንያት በተመለከተ ሁለት ዘገባ የተዘገበ ሲሆን፡-

የተወሰኑ ሙሽሪኮች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ሙሐመድ ሆይ! አላህ መልአክን ከብርሃን፤ አደምን ከጭቃ፤ ኢብሊስን ከእሳት፤ ሰማይን ከጭስ፤ እና ምድርን ከውሃ አረፋት ፈጠረ። እስቲ ጌታህን ከምን እንደተፈጠረ ግለጥልን? ከምንድን ነው የተሰራው? ከወርቅ ወይስ ከብር ወይስ ከነሀስ? ይበላል ወይስ ይጠጣል? ብለው በመጠየቃቸው ነው የወረደው። (ዋሒዲ፤ ሱዩጢ፤ አህመድና ቲርሚዚ)

ይህ አንቀፅ ሶስቱንም የተሳሳቱ ቡድኖች ማለትም፡-

ሀ. መላኢኮች የአላህ ሴት ልጆች ናቸው የሚሉትን የዐረብ አጋሪዎች፤

ለ. ዑዘይር የአላህ ልጅ ነው የሚሉት አይሁድና

ሐ. መሲሕ የአላህ ልጅ ነው የሚሉትን ክርስቲያኖችን በአንድ በቂና የማያዳግም መልስ ይሰጣል።

እሱን የሚመስል ምንም ነገር የለም «ለአላህ አምሳያዎችን አታድርጉ (መሳይ እንደሌለው) ያውቃል እናንተ ግን አታውቁም»

«ሰማያትንና ምድርን ፈጣሪ ነው። ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ከቤት እንስሳዎችም አይነቶችን (ወንዶችና ሴቶችን) ለእናንተ አደረገላችሁ። በእርሱ ያበዛችኋል። የሚመስለው ምንም ነገር የለም። እርሱ ሰሚና ተመልካች ነው»

«እርሱ የሰማያትና የምድር በሁለቱም መካከል ላለው ሁሉ ጌታ ነውና ተገዛው። እርሱንም በመገዛትም ላይ ታገስ ለእርሱ ሞክሼን ታውቃለህን?» (መርየም፡ 65) «ለእርሱም አንድም ብጤ የለውም» (አል-ኢኽላስ፡ 4) እንዳለው ሁሉ ይህን በግልፅ እንማራለን።

ነብዩ (ﷺ) ይህን በሱብሂ፤ በመግሪብ፤ በጠዋፍና በውትር ሱና ሶላቶች ላይ አዘወትረው ያነቧት እንደነበር በብዙ ሀዲስ ተዘግቧል። ሙስሊሞች ይህን አይነት ሱና በማስታወስ ሊተገበሩት ይገባል። ይህ አባባል ግን ምዕራፉ በመዲና መውረዱን ነው የሚያሳየውና በመካ የወረደ ለመሆኑ ደግሞ ከፍተኛ መረጃ ስላለ አይጣጣም።

✶2 (ሀ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ሙዓዝ ኢብኑ ጀበል እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ)፡- «ሙዓዝ ሆይ! አላህ በባሪያዎቹ ላይ ያለውን ሐቅ ታውቃለህን?» አሉ። እሱም «አላህና መልዕክተኛው ከማንም ይበለጥ ያውቃሉ» ብሎ መለሰ። እሳቸውም «የአላህ ሀቅ ባሪያዎቹ እርሱን ብቻ እንዲገዙና ከእርሱ ጋር አንዳች ነገር እንዳያመልኩ ነው» አሉ። ቀጠል አድርገውም «ሙዓዝ ሆይ! በአላህ ላይ ያለውን እነሱን የባሪያዎቹን ሐቅ ታውቃለህ?»ሲሉ ጠየቁት። እሱም «አላህና መልዕክተኛው ከማንም ይበልጥ ያውቃሉ»በማለት መለሰላቸው። እሳቸውም፡- «እነሱን ሐቅ እንዳይቀጣቸው ነው» አሉት።

(ለ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰዒድ አነስ እንዳስተላለፉት «አንድ ሰው ሌላ ሰው «ቁልሁወላሁ አሐድን»እየደጋገመ ሲቀራ ሰማው። በማለዳ ተነስቶ ወደ ነብዩ በመምጣት ክስተቱን ነገራቸው። የነገራቸውም ይህ የቁርኣን በቂ መስሎ ስላልታየው ነበር። እሳቸውም«ነፍሴ በእጁ በሆነችው አላህ እምላለሁ! በእርግጥ ይህ የቁርኣን ሲሶ አንድ ሶስተኛ ታህላለች» አሉት።

(ሐ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዓኢሻህ አነስ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) አንድ ቁርኣን የሚቀራው ሰው መሪ አድርገው ሰዎችን ወደ ዘመቻ ላኩ። ይህ ሰው ባልንጀራዎቹን ሶላት ሲያሰግዱ ሶላቱን «ቁልሁወላሁ አሐድን» በሚባለው የቁርኣን ያጠናቅቅ ነበር። ሰዎቹ ከዘመቻ ሲመለሱ ሁኔታውን ለነብዩ (ﷺ) ነገሯቸው። እሳቸውም «ለምን ይህን እንደሚያደርግ ጠይቁት» አሏቸው። ሰዎቹም ጠየቁት። እሱም ሲመልስ «ይህ እጅግ በጣም ሩህሩህ የሆነውን ጌታ መገለጫ ስለሆነ እሱን መቅራት ስለምወድ ነው»አላቸው። ነብዩም (ﷺ) «አላህ እሱንም በእርግጥ እንደሚወደው ንገሩት አሏቸው»

ሀ-አቡ የዕላ በዘገቡት ሐዲስ። ሰዒድ ኢብኑ ጁባይር እንዳስተላለፉት «የአል-መሰድ ምዕራፍ ሲወርድ አቡበክር ከነብዩ ጎን ተቀምጠው ሳሉ የአቡ ለሀብ ሚስት ነብዩን ፈለጋ መጣች። አቡበክርም ለነብዩ «እሷ ወደኛ ስትመጣ እርሶ በሌላ አቅጣጫ ቢሄዱ እመኛለሁ። ምናልባት ጉዳት ልታደርስብዎት ትችላለች» አሏቸው። እሳቸውም «በእኔና በርሷ መካከል ግርዶሽ አለ» አሉ። እሷም እሳቸውን አላየቻቸውም ነበርና ለአቡበከር «ያ ወዳጅህ በእኔ ላይ ግጥም ገጥሟል አሉ» አለቻቸው። አቡበክርም «በአላህ እምላለሁ! እርሱ ግጥም አይገጥምም» አሏት። እሷም «ይህን ታምንበታለህን?»ብላ ትታቸው ሄደች። አቡበክርም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አላየችትም» አሉ። ነብዩ (ﷺ) «መላዕክት እኔን ከርሷ ላይ ጋርዶኛል» አሉ።

**ከፍፁምነት ምዕራፍ ከአንቀፅ (1-3) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፡-**

1. አላህ የምንለዉን ሁሉ የሚሰማንና የምንሰራዉን ሁሉ የሚያውቅ መሆኑን፤
2. የአላህን አንድነትና ብቻውን ሊመለክ የሚገባው ብቸኛ አምላክ መሆኑን፤
3. ለፈጣሪ ልጅ፤ ሚስት፤ እሱን መሰል ቢጤ አለው ማለት መሰረተ ቢስ አባባል መሆኑን፤
4. አላህ ልጅ፤ ሚስት አለው ማለት ኩፍር (ክህደት) መሆኑን፤
5. የነብዩ መሐመድን (ﷺ) ነብይነትን ማረጋገጥ፤
6. አንድም ስልጣኑን መጋፋት የሚችል፤ ሌላ ተጋሪ የሌለው ብቸኛ አምላክ መሆኑን፤
7. አላህን በስሞቹና በባህሪያቱ ማወቅ ተገቢ መሆኑን እንማራለን።

## በአላህ ፈቃድ የፍፁምነት ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (113)
## የተፈልቃቂው ምዕራፍ
## (ሱረቱ አል-ፈለቅ)

سُورَةُ الفَلَقِ

የወረደው በመካ ነው። የምእራፉ አናቅፅ (5) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلۡفَلَقِ ١ مِن شَرِّ مَا خَلَقَ ٢ وَمِن شَرِّ غَاسِقٍ إِذَا وَقَبَ ٣
وَمِن شَرِّ ٱلنَّفَّٰثَٰتِ فِي ٱلۡعُقَدِ ٤ وَمِن شَرِّ حَاسِدٍ إِذَا حَسَدَ ٥

**1-5.** (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ)፣ በተፈልቃቂው ጎህ (በአልፈለቅ) ጌታ፤ ከፈጠረው ፍጡር ሁሉ ከፋት። ከሌሊትም ከፋት ባጨለመ ጊዜ፤ በተቋጠሩ ክሮች ላይ ተፊዎች ከሆኑት ደጋሚ ሴቶችም ከፋት፤ ከምቀኛም ከፋት፤ በተመቀኘ ጊዜ* እጠበቃለሁ በል።

* እነዚህ ሶስቱ ተከታታይ የመጨረሻ ምዕራፎች ነቢዩ (ﷺ) ሊተኙ ሲሉ በመዳፋቸው ላይ በመቅራትና መዳፋቸዉን ትንሽ ትንሽ በምራቃቸው በማርጠብ ፊታቸውንና የደረሱበትን አካላቸውን ሁሉ ያብሱ እንደነበር በቡኻሪ ተዘግቧል። እንደዚሁም ከአምስቱ የፈርድ ሶላቶች በኋላ አንዳንድ ጊዜ ያነቧቸው እንደነበርና በተለይም ከመግሪብና ከሱብሂ ሰላት በኋላ ሶስት ሶስት ጊዜ ያነቧቸው እንደነበር አቡዳዉድና ነሳኢ ዘግበዋል። እናም ሁሉም ሙስሊም ማህበረሰብ ይህንን የነብዩን ሱና ሊተገብረው ይገባል።

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሰኢድ አልኹድሪይ የአላህ መልዕክተኛ አልፈለቅ እና አንናስ ምዕራፎች እስኪወርዱ ድረስ ከአጋንንትና ከሰው ዓይን የአላህን ጥበቃ ለማግኘት በራሳቸው አባባል ይማፀኑት (በአላህ ይጠበቁ) ነበር። ምዕራፎቹ ከወረዱ በኋላ ግን ሌላውን አባባላቸውን ትተው በነዚህ ሱራወች መጠበቅ ጀመሩ ብለዋል።

**ከተፍለቅላቂው ምዕራፉ ከአንቀፅ (1-5) ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ:-**

1. እያንዳንዱ ሰው መጥፎ ድርጊት እንዲፈፅም ከሚያደርገው ሰይጣንም ሆነ አሳሳች ሰው መጠንቀቅ እንዳለበት፤
2. ከዚህ መሰሉ ችግር መጠበቅ የሚቻለው በአንድ አላህ ብቻ መሆኑን፤
3. መወስወስ (መሳሳት) በሰይጣን ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በእርጉም ሰዎችም ሊፈፀም እንደሚችል፤
4. ሰይጣንም ሆነ ተንኮለኛ ሰው ሰውን ሊያሳስቱ የሚችሉ ከአላህ በተዘናጋበት ጊዜ መሆኑን፤

5. የአላህን ብቸኛ አምላክነት ለማወቅ ፈጣሪነቱንና ንጉሱነቱን ማወቅ እንደሚገባ፤
6. ሰይጣን የሚባል እርኩስ መንፈስ መኖሩን ማወቅ እንዳለብን ከአናቅፅ እንማራለን።
7. ሰይጣን እንዳለ ሁሉ የሰው ሰይጣንም ሰወችን የሚያሳስት መጥፎ ተንኮለኛ እንዳለ እንረዳለን::

በአላህ ፈቃድ የተፍለቅላቂው ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

## ምዕራፍ (114)
## የሰዎች ምዕራፍ
## (ሱረቱ አን-ናስ)

سُورَةُ النَّاسِ

የወረደው በመካ ነው። የአናቅፅ ብዛት (6) ናቸው።

بِسۡمِ ٱللَّهِ ٱلرَّحۡمَٰنِ ٱلرَّحِيمِ

**በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ በጣም አዛኝ በሆነው (እጀምራለሁ)**

قُلۡ أَعُوذُ بِرَبِّ ٱلنَّاسِ ١ مَلِكِ ٱلنَّاسِ ٢ إِلَٰهِ ٱلنَّاسِ ٣ مِن شَرِّ ٱلۡوَسۡوَاسِ ٱلۡخَنَّاسِ ٤
ٱلَّذِي يُوَسۡوِسُ فِي صُدُورِ ٱلنَّاسِ ٥ مِنَ ٱلۡجِنَّةِ وَٱلنَّاسِ ٦

**1-6.** (መልክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!) በሰዎች ፈጣሪ (በአላህ) እጠበቃለሁ በል። የሰዎች ሁሉ ንጉስ በሆነው፤ የሰዎች አምላክ በሆነው፤ ብቅ እልም ባይ ከሆነው ጎትጓች (ሰይጣን) ክፋት*1 ከዚያ በሰዎች ልቦች ውስጥ የሚጎተጉት ከሆነው ከጋኔኖችም ከሰዎችም (ሰይጣናት በአላህ እጠበቃለሁ በል)*2።

✴1 ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፦ «የጀሃነም እሳት በመጥፎ ስሜቶችን በመስራት የተከበበች ስትሆን ጀነት ደግሞ ነፍሳችን ለመስራት በምትጠላው ኸይርና ለመስራት በማትፈልገው የተከበበች ነች»

✴2 እናታችን ዓኢሻህ ባስተላለፉትና ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ «የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) በማንኛውም ወቅት ወደ አልጋቸው ለመተኛት ሲሄዱ የ«አል. ኢኽላስ»ን፤ የአል. ፈለቅን» እና የ«አን-ናስን› ምዕራፎች ካነበቡ በኋላ መዳፎቻቸውን ላይ ምራቃቸውን እትፍ ካሉ በኋላ እጆቻቸው የሚደርሱባቸውን የሰውት ክፍሎች ያስቡ ነበር። እሳቸው ሲታመሙም እኔ እሳቸው ያደርጉት እንደነበረው እንዳደርግላቸው ያዙኝ ነበር» ብለዋል።

**ከሰዎች ምዕራፍ ከምናገኛቸው አንኳር ነጥቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ፦**

1. አላህ የነብዩችና የትክክለኛ አማኞች ብቸኛ መጠጊያ መሆኑን፤
2. ዳቢሎስ የሰው ልጆች ክፉ ጠላታቸው መሆኑን፤
3. የዳቢሎስን ትዕዛዝ የሚያስፈፅሙ አያሌ ረዳቶች ያሉት መሆኑንም እንረዳለን።

በአላህ ፈቃድ የሰዎች ምዕራፍ እዚህ ላይ አበቃ።

አላህ ሁሉን ያውቃል። በሰላም አስጀምሮ በሰላም ለመጨረስ ለአበቃኝ አላህ ቁጥር ስፍር የሌለው ምስጋና ይድረሰው። አላህ ሰላሙንና ረድኤቱን ለነቢዩ ሙሐመድ፤ ለንፁሃን ቤተሰቦቻቸው፤ ለሁሉም ባልደረቦቻቸውና እስከ ዐለም ፍፃሜ ድረስ የእነሱን መልካም ፈለግ ለሚከተሉ አማኞች ሁሉ ይሁን። አሚን።

# فهرس بأسماء السور وبيان المكي والمدني منها

## የምዕራፎችን ስሞች ማውጫና በመካና መዲና የወረዱ ምእራፎች ዝርዝር


| ተ.ቁ | ምዕራፍ (ሱራ) | ገጽ (ሰፍሐ) | መኪ.ያ/መደኒ.ያ | السورة |
|---|---|---|---|---|
| 1 | አል-ፋቲሓ | 1 | መኪ.ያ | الفاتحة |
| 2 | አል-በቀራ | 3 | መደኒ.ያ | البقرة |
| 3 | ኣሊ-ዒምራን | 104 | መደኒ.ያ | آل عمران |
| 4 | አል-ኒሳእ | 156 | መደኒ.ያ | النساء |
| 5 | አል-ማኢዳ | 212 | መደኒ.ያ | المائدة |
| 6 | አል-አንዓም | 252 | መኪ.ያ | الأنعام |
| 7 | አል-አዕራፍ | 293 | መኪ.ያ | الأعراف |
| 8 | አል-አንፋል | 335 | መደኒ.ያ | الأنفال |
| 9 | አት-ተውባ | 354 | መደኒ.ያ | التوبة |
| 10 | ዩኑስ | 398 | መኪ.ያ | يونس |
| 11 | ሁድ | 423 | መኪ.ያ | هود |
| 12 | ዩሱፍ | 450 | መኪ.ያ | يوسف |
| 13 | አር-ረዕድ | 472 | መደኒ.ያ | الرعد |
| 14 | ኢብራሒም | 484 | መደኒ.ያ | إبراهيم |
| 15 | አል-ሒጅር | 495 | መኪ.ያ | الحجر |
| 16 | አን-ነሕል | 505 | መኪ.ያ | النحل |
| 17 | አል-ኢስራእ | 531 | መኪ.ያ | الإسراء |
| 18 | አል-ከህፍ | 554 | መኪ.ያ | الكهف |
| 19 | መርየም | 577 | መኪ.ያ | مريم |
| 20 | ጧሃ | 592 | መኪ.ያ | طه |
| 21 | አል-አንቢያእ | 610 | መኪ.ያ | الأنبياء |
| 22 | አል-ሐጅ | 627 | መኪ.ያ | الحج |
| 23 | አል-ሙዕሙሚኑን | 645 | መኪ.ያ | المؤمنون |
| 24 | አን-ኑር | 660 | መደኒ.ያ | النور |
| 25 | አል-ፉርቃን | 681 | መኪ.ያ | الفرقان |
| 26 | አሽ-ሹዐራእ | 696 | መኪ.ያ | الشعراء |
| 27 | አን-ነምል | 714 | መኪ.ያ | النمل |

| ተ.ቁ | ምዕራፍ (ሱራ) | ገጽ (ሰፍሐ) | መኪያ/መደኒያ | السورة |
|---|---|---|---|---|
| 28 | አል-ቀሰስ | 729 | መኪያ | القصص |
| 29 | አል-ዐንከቡት | 745 | መኪያ | العنكبوت |
| 30 | አር-ሩም | 759 | መኪያ | الروم |
| 31 | ሉቅማን | 771 | መኪያ | لقمان |
| 32 | አስ-ሰጅዳ | 779 | መኪያ | السجدة |
| 33 | አል-አህዛብ | 785 | መደኒያ | الأحزاب |
| 34 | ሰበእ | 810 | መኪያ | سبإ |
| 35 | ፋጢር | 821 | መኪያ | فاطر |
| 36 | ያሲን | 832 | መኪያ | يس |
| 37 | አስ-ሳፋት | 842 | መኪያ | الصافات |
| 38 | ሷድ | 854 | መኪያ | ص |
| 39 | አዝ-ዙመር | 865 | መኪያ | الزمر |
| 40 | ጋፊር | 882 | መኪያ | غافر |
| 41 | ፉስ-ሲለት | 896 | መኪያ | فصِّلت |
| 42 | አሽ-ሹራ | 907 | መኪያ | الشورى |
| 43 | አዝ-ዙኽሩፍ | 919 | መኪያ | الزخرف |
| 44 | አድ-ዱኻን | 931 | መኪያ | الدخان |
| 45 | አል-ጃሲያ | 937 | መኪያ | الجاثية |
| 46 | አል-አህቃፍ | 944 | መኪያ | الأحقاف |
| 47 | ሙሐመድ | 953 | መደኒያ | محمد |
| 48 | አል-ፈትሕ | 962 | መደኒያ | الفتح |
| 49 | አል-ሑጁራት | 970 | መደኒያ | الحجرات |
| 50 | ቃፍ | 977 | መኪያ | ق |
| 51 | አዝ-ዛሪያት | 983 | መኪያ | الذاريات |
| 52 | አጥ-ጡር | 989 | መኪያ | الطور |
| 53 | አን-ነጅም | 995 | መኪያ | النجم |
| 54 | አል-ቀመር | 1002 | መኪያ | القمر |
| 55 | አር-ረህማን | 1007 | መደኒያ | الرحمن |
| 56 | አል-ዋቂዓ | 1014 | መኪያ | الواقعة |

| ተ.ቁ | ምዕራፍ (ሱራ) | ገጽ (ሰፍሐ) | መኪያ/መደኒያ | السورة |
|---|---|---|---|---|
| 57 | አል-ሃዲድ | 1020 | መደኒያ | الحديد |
| 58 | አል-ሙጃደላ | 1028 | መደኒያ | المجادلة |
| 59 | አል-ሐሽር | 1035 | መደኒያ | الحشر |
| 60 | አል-ሙምተሒና | 1042 | መደኒያ | الممتحنة |
| 61 | አስ-ሰፍ | 1049 | መደኒያ | الصف |
| 62 | አል-ጁሙዓ | 1053 | መደኒያ | الجمعة |
| 63 | አል-ሙናፊቁን | 1057 | መደኒያ | المنافقون |
| 64 | አት-ተጋቡን | 1061 | መደኒያ | التغابن |
| 65 | አጥ-ጦላቅ | 1066 | መደኒያ | الطلاق |
| 66 | አት-ተሕሪም | 1070 | መደኒያ | التحريم |
| 67 | አል-ሙልክ | 1074 | መኪያ | الملك |
| 68 | አል-ቀለም | 1079 | መኪያ | القلم |
| 69 | አል-ሐቅቃ | 1085 | መኪያ | الحاقة |
| 70 | አል-መዓሪጅ | 1090 | መኪያ | المعارج |
| 71 | ኑሕ | 1094 | መኪያ | نوح |
| 72 | አል-ጂን | 1098 | መኪያ | الجن |
| 73 | አል-ሙዝዘሚል | 1102 | መኪያ | المزمل |
| 74 | አል-ሙድደሲር | 1106 | መኪያ | المدثر |
| 75 | አል-ቂያማ | 1111 | መኪያ | القيامة |
| 76 | አል-ኢንሳን | 1115 | መደኒያ | الإنسان |
| 77 | አል-ሙርሰላት | 1120 | መኪያ | المرسلات |
| 78 | አን-ነበእ | 1124 | መኪያ | النبإ |
| 79 | አን-ናዚዓት | 1128 | መኪያ | النازعات |
| 80 | ዐበሰ | 1131 | መኪያ | عبس |
| 81 | አት-ተክዊር | 1134 | መኪያ | التكوير |
| 82 | አል-ኢንፊጧር | 1137 | መኪያ | الانفطار |
| 83 | አል-ሙጠፊፊን | 1140 | መኪያ | المطففين |
| 84 | አል-ኢንሽቃቅ | 1143 | መኪያ | الانشقاق |
| 85 | አል-ቡሩጅ | 1145 | መኪያ | البروج |

| ተ.ቁ | ምዕራፍ (ሱራ) | ገጽ (ሰፍሐ) | መኪያ/መደኒያ | السورة |
|---|---|---|---|---|
| 86 | አጥ-ጧሪቅ | 1149 | መኪያ | الطارق |
| 87 | አል-አዕላ | 1151 | መኪያ | الأعلى |
| 88 | አል-ጋሺያ | 1153 | መኪያ | الغاشية |
| 89 | አል-ፈጅር | 1155 | መኪያ | الفجر |
| 90 | አል-በለድ | 1158 | መኪያ | البلد |
| 91 | አሽ-ሸምስ | 1160 | መኪያ | الشمس |
| 92 | አል-ለይል | 1162 | መኪያ | الليل |
| 93 | አድ-ዱሓ | 1165 | መኪያ | الضحى |
| 94 | አሽ-ሸርህ | 1167 | መኪያ | الشرح |
| 95 | አት-ቲን | 1169 | መኪያ | التين |
| 96 | አል-ዐለቅ | 1170 | መኪያ | العلق |
| 97 | አል-ቀድር | 1173 | መኪያ | القدر |
| 98 | አል-በይይናህ | 1175 | መደኒያ | البينة |
| 99 | አዝ-ዘልዘላ | 1177 | መደኒያ | الزلزلة |
| 100 | አል-ዓዲያት | 1179 | መኪያ | العاديات |
| 101 | አል-ቃሪዓ | 1181 | መኪያ | القارعة |
| 102 | አት-ተካሱር | 1183 | መኪያ | التكاثر |
| 103 | አል-ዐስር | 1185 | መኪያ | العصر |
| 104 | አል-ሑመዛ | 1187 | መኪያ | الهمزة |
| 105 | አል-ፊል | 1188 | መኪያ | الفيل |
| 106 | ቁረይሽ | 1190 | መኪያ | قريش |
| 107 | አል-ማዑን | 1191 | መኪያ | الماعون |
| 108 | አል-ከውሠር | 1193 | መኪያ | الكوثر |
| 109 | አል-ካፊሩን | 1194 | መኪያ | الكافرون |
| 110 | አን-ነስር | 1196 | መኪያ | النصر |
| 111 | አል-መሰድ | 1198 | መኪያ | المسد |
| 112 | አል-ኢኽላስ | 1199 | መኪያ | الإخلاص |
| 113 | አል-ፈለቅ | 1201 | መኪያ | الفلق |
| 114 | አን-ናስ | 1203 | መኪያ | الناس |

إنّ وزارة الشّؤون الإسلاميّة والدّعوة والإرشاد
في المملكة العربيّة السّعوديّة
المشرفة على
مجمّع الملك فهد لطباعة المصحف الشّريف
في المدينة المنوّرة
إذ يسرُّها أن يُصدر المجمّع هذه الطّبعة من
ترجمة معاني القرآن الكريم
إلى اللُّغة الأمهرية
تسأل الله أن ينفع بها النّاس
وأن يجزي
خادم الحرمين الشّريفين الملك سلمان بن عبدالعزيز آل سعود
أحسن الجزاء على جهوده العظيمة في نشر كتاب الله الكريم
والله وليّ التّوفيق

በሳውዲ አረቢያ የሚገኘው የእስልምና የዳዕዋና የመምሪያ ጉዳዮች ሚኒስቴር
በመዲነተል ሙነወራህ በሚገኘው የንጉስ ፈህድ የተከበረው ቁርኣን ማተሚያ ድርጅት ይህን የአማርኛ የቁርኣን ትርጉም አሳትሞ ሲያቀርብላችሁ በደስታ ነው።
አላህ በዚህ ቁርኣን ሰዎችን ተጠቃሚ እንዲያደርጋቸው እንማጸናለን።
እንደዚሁም የሁለት የተከበሩ መስጅዶች አስተዳደሪ የሆኑትን ንጉስ ሰልማን ቢን ዓብዱል ዓዚዝ ኣል ሱዑድን የተከበረ የአላህን ቁርኣን በማሰራጨታቸው መልካም ጀዛ (ምንዳ) አላህ እንዲለግሳቸው እንማጸናለን።
አላህ ትክክለኛውን የመምራት ባለቤት ነው።

بعون الله وتوفيقه
تم طبع هذه الترجمة لمعاني
القرآن الكريم في مجمع الملك فهد
لطباعة المصحف الشريف بالمدينة المنورة
بإشراف وزارة الشؤون الإسلامية
والدعوة والإرشاد في
المملكة العربية السعودية
عام ١٤٤٤هـ

حقوق الطبع محفوظة
لمجمع الملك فهد لطباعة المصحف الشريف

---

ص.ب ٦٢٦٢ - المدينة المنورة

www.qurancomplex.gov.sa
contact@qurancomplex.gov.sa

በአላህ እርዳታ እና ስኬት ይህ
የተከበረ ቁርአን ትርጉሞች
በሳውዲ አረቢያ ውስጥ እስልምና
ጉዳዮች ፣ ጥሪ እና መመሪያ ሚኒስቴር
ቁጥጥር ስር በመዲና ውስጥ የቅዱስ
ቁርኣን ማተሚያ ቤት ታተመ፡፡
በ 1444 ሂ.ሂ

የቅጂ መብት የተጠበቀ ነው
ኪንግ ፋህድ ኮምፕሌክስ የተከበረው ቁርአን ህትመት

ፖ.ሳ.ቁ. 6262 - መዲና

www.qurancomplex.gov.sa
contact@qurancomplex.gov.sa

ⓒ **مجمع الملك فهد لطباعة المصحف الشريف، ١٤٤٤هـ**
فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر

مجمع الملك فهد لطباعة المصحف الشريف
**ترجمة معاني القرآن الكريم إلى اللغة الأمهرية.** /مجمع الملك
فهد لطباعة المصحف الشريف - ط١ - المدينة المنورة، ١٤٤٤هـ

١٢٣٢ص؛ ١٣,٥ × ١٩,٣سم

**ردمك:** ٤-٧١-٨٣١١-٦٠٣-٩٧٨

١- القرآن - ترجمة - اللغة الأمهرية　　أ. العنوان
ديوي ٢٢١,٤٩٣٥　　١٤٤٤/٣٧٠٠

**رقم الإيداع:** ١٤٤٤/٣٧٠٠

**ردمك:** ٤-٧١-٨٣١١-٦٠٣-٩٧٨

9 786038 311714

**تصفح الترجمة**

**ትርጉሙን ቃኝ**